*መጽሐፍ ቅዱስን ሊረዱት ይችላሉ!*

# መዝሙር፡ የእስራኤላዊያን መንፈሳዊ መዝሙር

*ቦብ አትሊ*

*የትርጓሜ ፕሮፌሰር*

*(የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ)*

የጥናት መመሪያ ተከታታይ ሐተታ
ብሉይ ኪዳን፣ ቅጽ 9ለ

BIBLE LESSONS INTERNATIONAL
MARSHALL, TEXAS
2013

**www.BibleLessonsIntl.com**
**www.freebiblecommentary.org**

# ማውጫ

በዚህ ሐተታ ውስጥ ጥቅም ላይ  የዋሉ ሞያዊ ቃላት አጭር መግለጫ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . x
ትርጓሜው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የዕብራይስጥ ግሣዊ ቅርጾች ግልጽ ማብራሪያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . xi
ሐተታው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ አሕጽሮተ ቃላት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . xv
የጸሐፊው መልእክት:ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል? . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . xvii
ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ: . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .xix
የዕብራይስጥ ቅኔ መግቢያ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . xxv
መዝሙር  መግቢያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .1
መዝሙር 1 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .7
መዝሙር 2 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 20
መዝሙር 3 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .31
መዝሙር 4 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .35
መዝሙር 5 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 41
መዝሙር 6 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 46
መዝሙር 7 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 49
መዝሙር 8 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 57
መዝሙር 9 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 62
መዝሙር 10 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 72
መዝሙር 11 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .76
መዝሙር 12 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .81
መዝሙር 13 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 89
መዝሙር 14 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 92
መዝሙር 15 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 96
መዝሙር 16 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 99
መዝሙር 17 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 104
መዝሙር 18 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 109
መዝሙር 19 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 121
መዝሙር 20 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 129
መዝሙር 21 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 135
መዝሙር 22 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 139
መዝሙር 23 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 146
መዝሙር 24 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 154
መዝሙር 25 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 158
መዝሙር 26 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .165
መዝሙር 27 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 171
መዝሙር 28 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .177

መዝሙር 29 ........ 181
መዝሙር 30.. ........ 187
መዝሙር 31. ........ 194
መዝሙር 32. ........ 201
መዝሙር 33 .. ........ 206
መዝሙር 34. ........ 211
መዝሙር 35 . .. ........ 218
መዝሙር 36 . .. ........ 224
መዝሙር 37 . .. ........ 228
መዝሙር 38 . .. ........ 238
መዝሙር 39 . . . . . .. ........ 244
መዝሙር 40 . .. ........ 249
መዝሙር 41. . . . .. ........ 255
መዝሙር 42 . . .. ........ 259
መዝሙር 43 . . .. ........ 264
መዝሙር 44 . . . . .. ........ 267
መዝሙር 45 . . . . .. ........ 274
መዝሙር 46 . . . .. ........ 279
መዝሙር 47 . . .. ........ 283
መዝሙር 48. ........ 287
መዝሙር 49. ........ 291
መዝሙር 50. ........ 297
መዝሙር 51 ........ 310
መዝሙር 52 ........ 320
መዝሙር 53. ........ 325
መዝሙር 54 ........ 327
መዝሙር 55. ........ 330
መዝሙር 56. ........ 335
መዝሙር 57 ........ 338
መዝሙር 58. ........ 343
መዝሙር 59. ........ 346
መዝሙር 60 ........ 351
መዝሙር 61 ........ 355
መዝሙር 62 ........ 358
መዝሙር 63 ........ 361
መዝሙር 64 ........ 364
መዝሙር 65 ........ 372

መዝሙር 66.. 378
መዝሙር 67. 384
መዝሙር 68. 387
መዝሙር 69. 397
መዝሙር 70. 405
መዝሙር 71 408
መዝሙር 72. 414
መዝሙር 73 .. 420
መዝሙር 74. 427
መዝሙር 75. 434
መዝሙር 76. 438
መዝሙር 77. 443
መዝሙር 78. 448
መዝሙር 79. 459
መዝሙር 80. 464
መዝሙር 81.. 469
መዝሙር 82 .. 473
መዝሙር 83 477
መዝሙር 84 482
መዝሙር 85 487
መዝሙር 86. 491
መዝሙር 87. 497
መዝሙር 88. 500
መዝሙር 89. 505
መዝሙር 90. 514
መዝሙር 91. 520
መዝሙር 92. 524
መዝሙር 93 .. 528
መዝሙር 94 531
መዝሙር 95. 535
መዝሙር 96. 540
መዝሙር 97. 545
መዝሙር 98. 549
መዝሙር 99. 553
መዝሙር 100. 558
መዝሙር 101. 561
መዝሙር 102. 565

መዝሙር 103. . . . . . 570
መዝሙር 104 . . . . . .576
መዝሙር 105 . . . . . . 584
መዝሙር 106 . . . . . . 593
መዝሙር 107 . . . . . .604
መዝሙር 108. . . . . . 611
መዝሙር 109 .. . . . . .613
መዝሙር 110 .. . . . . . 621
መዝሙር 111 . .. . . . . 625
መዝሙር 112 .. . . . . .629
መዝሙር 113 .. . . . . . 633
መዝሙር 114 .. . . . . .636
መዝሙር 115 .. . . . . .634
መዝሙር 116 .. . . . . .643
መዝሙር 117 .. . . . . . 647
መዝሙር 118 .. . . . . . 649
መዝሙር 119. . . . . . .656
መዝሙር 120 .. . . . . . 686
መዝሙር 121 .. . . . . . 688
መዝሙር 122. . . . . . . 691
መዝሙር 123 . . .. . . . . 694
መዝሙር 124 . . . . . . 696
መዝሙር 125. . . . . . . 698
መዝሙር 126. . . . . . . 701
መዝሙር 127. . . . . . . 704
መዝሙር 128. . . . . . . 707
መዝሙር 129. . . . . . . 710
መዝሙር 130 .. . . . . . 713
መዝሙር 131. . . . . . . 716
መዝሙር 132 .. . . . . . 718
መዝሙር 133. . . . . . . 723
መዝሙር 134 .. . . . . . 726
መዝሙር 135. . . . . . . 728
መዝሙር 136 .. . . . . . 732
መዝሙር 137 .. . . . . . 736
መዝሙር 138 .. . . . . . 740
መዝሙር 139. . . . . . . 744

መዝሙር 140 . .. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .752
መዝሙር 141 .. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .756
መዝሙር 142. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 760
መዝሙር 143. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 763
መዝሙር 144. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 768
መዝሙር 145. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 773
መዝሙር 146. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 778
መዝሙር 147 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 781
መዝሙር 148. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 785
መዝሙር 149 . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 789
መዝሙር 150. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 793
መግለጫ ሁለት፡ የእምነት መግለጫ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 795

# ልዩ ርዕሶች የይዘት ማውጫ


የመለኮት ስሞች 12:1 . . . . 4

የእግዚአብሔር ራዕይ መግለጫ ቃላት (ዘዳግምንና መዝሙርን በመጠቀም) . . . . 12

ጽድቅ. . . . 15

ማወቅ (ባብዛኛው ዘዳግምን እንደ ምሳሌ በመጠቀም). . . . .16

ሙታን የት ናቸው?. . . . 17

የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ . . . . 21

መሬት፣ አገር፣ምድር. . . . 22

መሲሕ. . . . .23

የሚመጣው ልዩው መጠሪያዎች . . . . 23

እግዚአብሔር እንደ ሰው ተገልጧል (አንትሮፖሞርፊያዊ ቋንቋ) . . . . 25

ሰማይ . . . . 25

የእግዚአብሔር ልጅ . . . . 26

አሀዳዊነት . . . . .27

ድኅነት (መዳን). . . . 33

ልብ . . . . 38

መጽሐፍ ቅዱሳዊ አዝማሚያ በአልኮል እና በአልኮለኝነት . . . . 38

ደግነት (ሄሰድHESED) . . . . 43

ጥላ ለጥበቃና ለክብካቤ ዘይቤነት . . . . .44

የያህዌ "ስም". . . . .45

አናብስት በብሉይ ኪዳን. . . . 50

እጅ (ከሕዝቅኤል ላይ የተገለጸ) . . . . 51

ንስሃ መግባት በብሉይ ኪዳን. . . . 53

መፅናት . . . . .54

የጨረቃ አምልኮ . . . . 60

አስደናቂ ነገሮች (פלא) . . . . 63

ዘላለም (ኦላም). . . . 65

ሁለቱ የእግዚአብሔር መጻሕፍት. . . . 66

ፈራጅ፣ ፍርድ፣ እና ፍትሕ ( פטש) ኢሳይያስ ላይ. . . . .67

የእስራኤል አምላክ ባሕርያት . . . . 68

እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ ይፈትናል. . . . .78

በዚያን ቀን . . . . .78

እሳት (ቢዲቢ 77) . . . . .79

ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ እና ታማኝነት በብሉይ ኪዳን (אמן) . . . . 82

ተምሳሌት (ምልክት) ቁጥሮች በቅዱስ ቃሉ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 86
ርኵሰት (ጸያፍ) (ብኪ). . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .93
እስራኤል (ስሙ). . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 95
ቅዱስ (קדוש) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 100
ኪሩቤል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 113
ነውር የሌለው፣ ንጹሕ፣ ኃጢአት የሌለበት፣ ያለ ነውር. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 115
ክብር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 122
ተመስጦ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .124
መዋጀት/ መቤዠት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 126
ዮም. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 130
መመካት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 133
ባዶ፣ ከንቱ፣ ሐሰት፣ ምናምንነት (ቢዲቢ 996) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 156
ኪዳን (**ברית**) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 161
መመረጥ/ቅድመ ውሳኔ (መታደል) እና የሥነ መለኮት ሚዛን አስፈላጊነት. . . . . . . . . . . . . . .162
ትንሣኤ. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 165
ክህደት (አፈሰቴማይ). . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 168
“የእግዚአብሔር ልጆች” በዘፍጥረት 6. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 182
ፈውስ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነውን፣ ለየዘመናቱ?. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 188
ለሞት የሚያበቃ ኃጢአት ምንድነው?. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 189
የኀዘን ሥነ-ሥርዓት. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .192
እስትንፋስ፣ ነፋስ፣ መንፈስ ( **רוח** እና *pneuma*) . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .196
የእግዚአብሔር መልአክ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 213
የፍፃሜ ጊዜያት ክስተቶች ለምን አከራካሪ ሆኑ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .229
ሰይጣን. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 242
ክንድ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 246
አሜን . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .258
ቅድመ-እስራኤላውያን የፍልስጥኤም ነዋሪዎች. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 268
የያህዌ የጸጋ ድርጊቶች ለእስራኤል. . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 273
በእስራኤል ጥቅም ላይ የሚውሉ ቀንዶች . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 285
መሥዋዕት በሜሶፖታሚያ እና እስራኤል እና ጠቀሜታው . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .300
መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .314
ማረጋገጫ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 315
የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 316
ሥላሴ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 317

የሰው ንግግር . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .321
የያህዌ የኪዳን መስፈርት ለእስራኤል . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 352
ውጤታማ ጸሎት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 365
የምልጃ ጸሎት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 366
ያልተወሰነ ሆኖም የተወሰነ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 368
ስለይቅርታ የሚናገሩ ቃላት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 374
አብርሆት . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .380
መጠጊያ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 409
ኀፍረት (ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116) በሥነ-መለኮታዊ መልኩ . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . .409
ኢጋንታዊ (ርኩስ መንፈስ). . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . . 416

## "መጽሐፍ ቅዱስን መረዳት ትችላለህ" በሚለው የብሉይ ኪዳን ተከታታይ ትርጓሜ ሐተታ ጥቅም ላይ የዋሉ ሞያዊ ቃላት አጭር መግለጫ

የቃላት

በርካታ በጣም ጥሩ የሆኑ የጥንታዊ ዕብራይስጥ መዝገበ ቃላት ይገኛሉ።

ሀ. *የዕብራይስጥና እንግሊዝኛ የብሉይ ኪዳን የቃላት ዝርዝር* በ ፍራንሲስ ብራውን፣ ኤስ. አር. ድራይቨር፣ እና ቻርለስ ኤ. ብሪግስ። እሱም የተመሠረተው በጀርመን የቃላት ዝርዝር በዊሊየም ጌሴኒዩስ። እሱም ቢዲቢ በሚል ምሕጻረ ቃል ይታወቃል።

ለ. *የዕብራይስጥና አራማዊ የብሉይ ኪዳን የቃላት ዝርዝር* በሉድዊንግ ኮህለር እና ዋልተር ባዩምጋርትነር፣ በኤም. ኢ. ጄ. ሪቻርድሰን የተተረጎመ። እሱም ኬቢ በሚል ምሕጻረ ቃል ይታወቃል።

ሐ. *የዕብራይስጥና አራማዊ የብሉይ ኪዳን የቃላት ዝርዝር* በዊሊየም ኤል. ሆላዴይ እናም ከላይ ካለው የጀርመን የቃላት ዝርዝር ላይ የተመሠረተ።

መ. አዲሱ ባለ አምስት ቅጽ *ሥነ መለኮታዊ የቃላት ጥናት አዲሱ ዓለም አቀፍ የብሉይ ኪዳን ሥነ መለኮት እና ትርጓሜ፣* በዊሊየም ኤ. ቫን ጂመራን። እሱም ኒዶቲ በሚል ምሕጻረ ቃል ይታወቃል።

ትርጉም ያለው የቃላት ልዩነት በሚኖርበት ጊዜ በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞችን ለማሳየት ሞክሬአለሁ (አአመመቅ፣ አኪጀት፣ አየተመት፣ አእት፣ አኢመቅ) ከሁለቱም "ቃል በቃል" እና "የተለወጠ አቻ" ትርጓሜዎችን (ጎርዶን ፊ እና ዳግላስ ስቱዋርት፣ *መጽሐፍ ቅዱስን ከነሙሉ ጠቀሜታው እንዴት ማንበብ ይቻላል፣* ገጽ 28-44)።

ሰዋሰዋዊ

ሰዋሰዋዊ መለያው ዘወትር የተመሠረተው በጆን ጆሴፍ አውንስ *የብሉይ ኪዳን የትንታኔ ቁልፍ* በአራት ቅጽ ነው። ይህም በቤንጃሚን ዴቪድሰን *የብሉይ ኪዳን ትንታኔ፣ የዕብራይስጥና ከለዳውያን የቃላት ዝርዝር* በሚለው እንዲቃኝ ተደርጓል።

ሌለኛው ጠቃሚ ምንጭ፣ ለሰዋሰዋዊውም ሆነ ለአገባብ መልኩ፣ እሱም "መጽሐፍ ቅዱስን ልትረዳው ትችላለህ" በሚለው ተከታታይ ጽሑፍ በአብዛኞቹ የብኪ ቅጾች ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን፣ እሱም "ለተርጓሚዎች ተከታታይ ጽሑፍ ጠቀሜታ"፣ ከተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ ነው።

ጽሑፋዊ

እኔ ተመስጧዊ ለሆነው ለዕብራይስጥ ተናባቢ ጽሑፍ አትኩሮት አለኝ (ለምሥጢራዊ ጽሑፍ አናባቢ ሳይሆን፣ ለማመልከትም ሆነ አስተያየት ለመስጠት)። በሁሉም የእጅ ጽሑፎች፣ ጥንታዊ ጽሑፎች አጠያያቂ ምንባቦች አሏቸው። ይህም የሆነበት ምክንያት

ሀ. *ሃፓክስ ሌጎሜና* (በዕብራይስጥ ብኪ አንድ ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ)

ለ. *ፈሊጣዊ ቃላት* (ቃላትና ሐረጋት፣ ጥሬ ትርጉማቸው የጠፋ)

ሐ. *ታሪካዊ ርግጠኝነት የሌላቸው* (ስለ ጥንታዊው ዓለም ያለን መረጃ እጥረት ስላለበት)

መ. ብዙሐ-ሴማዊ የፍቺ መስክ ውስን የዕብራይስጥ መዝገበ ቃላት መኖሩ

ሠ. የቀድሞዎቹ ጸሐፍት የእጅ ጽሑፍ፣ በጥንታዊ የዕብራይስጥ ጽሑፎች ላይ የተያያዙ ችግሮች

ረ. የዕብራይስጥ ጸሐፊዎች በግብፅ የሠለጠኑት፣ እነሱም ጽሑፎቹን ለማሻሻል ነጻነት የሚሰማቸው፣ በሚቀዱበት ጊዜ ለዘመናቸው የተሟላ እንዲሆኑና የሚረዱ እንዲሆኑ በማድረጋቸው (NIDOTTE ገጽ 52-54)።

በርካታ የዕብራይስጥ ቃላት እና ጽሑፎች ምንጮች ከምሥጢራዊ ጽሑፋዊ ባህል ውጭ ይገኛሉ።

ሰማሪያዊ ፔንታቲዩች
የሙት ባሕር ጥቅሎች
የ ናሽ ፓፒረስ (አሥርቱ ትዕዛዛት)
የ ስቨሩስ ጥቅል (ፔንታቱክ)
አንዳንድ የኋለኛ ሳንቲሞች፣ ደብዳቤዎች፣ እና ሸክላ (ለጽሑፍ ያገለግሉ የነበሩ ያልተተኮሱ የሸክላ ስብርባሪዎች)

ነገር ግን በአብዛኛው ክፍል፣ በብኪ የእጅ ጽሑፍ ምድቦች የሉም፣ በግሪክ አኪ የእጅ ጽሑፎች እንዳሉት። አጠር ላለ ጽሑፍ፣ በጽሑፉ ተጨባጭነት፣ እሱም በምሥጢራዊ ጽሑፍ (የ900 ዓ.ም) "የብሉይ ኪዳን ጽሑፍ ተጨባጭነት" በብሩስ ኬ. ዋልተኬ በኒዶቴ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 51-67 ተመልከት።

ጥቅም ላይ የዋለው *የዕብራይስጡ ጽሑፍ ቢብሊያ ሔብራይካ ስቱትጋርቴንሲያ* ከጀርመን የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ፣ 1997፣ እሱም በሌሊንግራድ ኮዴክስ ላይ የተመሠረተ ነው (1009 ዓ.ም)። ከጊዜ ወደ ጊዜ የጥንት ትርጉሞች (ግሪክ፣ ሴፕቱዋጂንት፣ አዋሚክ ታርጉምስ፣ ሶሪያዊ ፔሺታ፣ እና ላቲን ቫልጌት) ተቃኝተዋል፣ ዕብራይስጡ አሻሚ ወይም በግልጽ አወዛጋቢ ሲሆን።

# ትርጓሜው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ የዕብራይስጥ
# ግሣዊ ቅርጾች ግልጽ ማብራሪያ

የዕብራይስጥ አጭር ታሪካዊ እድገት

ዕብራይስጥ የሴማቲክ (ሴማዊ) የደቡባዊ ምዕራብ እስያ ቋንቋ ቤተሰብ ክፍል ነው። ስሙ (በዘመናዊ ሊቃውንት የተሰጠው) የመጣው ከኖኅ ልጅ ከሴም ነው (ዘፍ. 5፡32፤ 6፡10)። የሴም ዝርያዎች በዘፍ. 10፡21-31 ተዘርዝረዋል፣ እንደ ዓረቦች፣ ዕብራውያን፣ ሶርያውያን፣ አርማናውያን፣ እና ሴሪናውያን። በተጨባጭ፣ አንዳንድ ሴማዊ ቋንቋዎች በካም የዘር ሐረግ በተዘረዘሩት ሕዝቦች ይነገሩ ነበር (ዘፍ. 10፡6-14)፣ ከነዓን፣ ፍንቄአዊ፣ እና ኢትዮጵያ።

ዕብራይስጥ የእነዚህ ሰሜን ምዕራብ ምድብ ሴማዊ ቋንቋዎች ክፍል ነው። ዘመናዊ ሊቃውንት የዚህ የጥንት የቋንቋ ምድብ ናሙናዎችን ያገኙት፡

ሀ. አሞራውያን (የማሪ የገበታ ጽሑፎች ከ18ኛ ክፍለ ዘመን ዓ.ዓ በአካድያን)

ለ. ከነዓናዊ (ራስ ሻምራ የገበታ ጽሑፎች ከ15ኛ ክፍለ ዘመን በዩጋሪቲክ)

ሐ. ከነዓናዊ (አማርና ደብዳቤዎች ከ14ኛ ክፍለ ዘመን በከነዓናዊ አካዲያን)

መ. ፍንቄአውያን (ዕብራይስጥ የፎንቄውያንን ፊደላት ይጠቀማል)

ሠ. ሞአባዊ (ሜሻ ድንጋይ፣ 840 ዓ.ዓ)

ረ. አራምኛ (የፋርስ ሰፊ ግዛት ብሔራዊ ቋንቋ ነበር ዘፍ. 31፡47 ጥቅም ላይ የዋለ [2 ቃላት]፤ ኤር. 10፡11፤ ዳን. 2፡4ለ-6፤ 7፡28፤ እዝራ 4፡8-6፡18፤ 7፡12-26 እንዲሁም በአይሁድ ይነገር ነበር፣ በአንደኛው ክፍለ ዘመን በፍልስጥኤም)

የዕብራይስጡ ቋንቋ "የከነዓን ከንፈር" ተብሎ ይጠራል በኢሳ. 19፡18። እሱም በመጀመሪያ የሚጠራው "ዕብራይስጥ" ተብሎ ነው፣ በጥበብ መጽሐፍ መግቢያ ላይ (የቢን ሲራክ ጥበብ) በግምት 180 ዓ.ዓ (እና ሌሎች የጥንት ስፍራዎች፣ *መልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት*፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 205)። እሱም በእጅጉን የሚዛመደው ከሞአባዊ እና በዩጋሪቲ በሚነገረው ቋንቋ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጭ የሚገኙት ጥንታዊ ዕብራይስጥ ምሳሌዎች የሚሆኑት

የጋዜር ዘመን መቁጠሪያ፣ 925 ዓ.ዓ (የትምህርት ቤት ልጅ ጽሑፍ)

የሲሎም ጽሑፍ፣ 705 ዓ.ዓ (የዋሻ ጽሑፎች)

ሰማሪያዊ ኦስትራካ፣ 770 ዓ.ዓ (በተሰባበረ ሸክላ የግብር መዝገቦች)

ላቺሽ ደብዳቤዎች፣ 587 ዓ.ዓ (የጦርነት መገናኛዎች)

የመቃብያን ሳንቲሞች እና ማኅተሞች

አንዳንድ የሙት ባሕር ጥቅል ጽሑፎች

የቁጥር ጽሑፎች ("ቋንቋዎች [ዕብራይስጥ]፣ ኤቢዲ 4፡203)

እሱ፣ እንደሌሎቹ ሴማዊ ቋንቋዎች፣ ከሦስት ተናባቢዎች የተመሠረቱ ቃላት ባሕርይ ያለው ነው (የሦስት ተናባቢ ሥሮች)። እሱ የማይተጣጠፍ ቋንቋ ነው። ባለ ሦስት ተናባቢ የቃሉን ዋነኛ ፍቺ ይይዛል፣ ቅድመ ቅጥያ፣ ድሕረ ቅጥያ ወይም የውስጥ ምዕላዶች (ተጨማማሪዎች) ሲደረጉበት፣ ይሄም የአገባቡን ተግባር ያመላክታል (አናባቢዎች ኋላ ላይ ነው የሚጨመሩት፣ ሱ ግሪን፣ የሥነ ቋንቋ (ሊንጉስቲክ) ትንታኔ የዕብራይስጥ ቅዱሳት መጻሕፍት፣ ገጽ 46-49)።

የዕብራይስጥ መዝገበ ቃላት በስድ ንባብና በቅኔ መካከል ልዩነትን ያመላክታል። የቃላት ትርጉሞች ከቃላዊ ሥርወ ቃል ጋር ይያያዛል (ከሥነ ቋንቋዊ መነሻ ያልሆነ)። የቃላት አግባብ እና የድምጽ አግባብ የተለመዱ ናቸው (ፓሮኖማሲያ)።

የአንቀጽ ገጽታዎች

ሀ. ግሦች

ሁነኛው የቃላት ቅደም ተከተል የሚሆነው ግሥ፣ ተውላጠ ስም፣ ባለቤት (ከአጉሊዎች ጋር)፣ ተሳቢ (ከአጉሊዎች ጋር)። መሠረታዊው ምልክት አልባ ግሥ የተጠናቀቀው ነው፣ ተባዕታይ ጾታ፣ ነጠላ ቁጥር ቅርጽ ነው። የዕብራይስጥና አራማዊ የቃላት ዝርዝሮች የተቀመሩት እንዲህ ነው። ግሦች ረብተው የሚያሳዩት

ቁጥር— ነጠላ፣ የብዙ፣ ሁለቱንም

ጾታ— ተባዕታይ እና አንስታይ (ገለልተኛ የለውም)

ሁኔታን— አመላካች፣ ሁኔታን ገላጭ፣ ተተኳሪ (አስገዳጅ) በምስያነት ከዘመናዊው የምዕራባውያን ቋንቋ ጋር፣ የድርጊቱ ዝምድና ከተጨባጩ ጋር ነው)

ጊዜ (ገጽታ)

ሀ. የተጠናቀቀ፣ ይህም የሚያሳየው የተጠናቀቀ፣ የሱም አግባብ አጀማመሩን፣ ቀጣይነቱን፣ እና አደማደሙን ነው የአንድን ድርጊት። ይህ ቅርጽ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለሀላፊ ጊዜ ነው፣ ነገሩ የተደረገበት።

ጄ. ዋሽ ዋትስ፣ *በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን አገባብ ጥናት* ላይ፣ የሚለው

"በተጠናቀቀ የተገለጠ የነጠላ አጠቃሎሽ እንደ ትክክለኛ ይወሰዳል። ያልተጠናቀቀ ምናልባት ሊሆን የሚችለውን የምስል ሁኔታ ያሳያል ወይም የሚፈለገውን ወይም ተስፋ የሚደረገውን ነው፣ ነገር ግን የተጠናቀቀው እንደ ትክክለኛ፣ እውናዊና ርግጠኛነት ያመላክታል" (ገጽ 36)።

ኤስ. አር. ድራይቨር፣ *የዕብራይስጥ ጊዜያት አጠቃቀም ጽሑፍ*፣ እንዲህ ይገልጸዋል፡

“የተጠናቀቀው ጥቅም ላይ የሚውለው ድርጊትን ለማመልከት ነው፣ እሱም ወደፊት ሊያዝ የሚችለውን ሲሆን፣ ግን የሚታየው ጥገኛ ሆኖ ነው፣ በዚህ በማይለወጥ ውሳኔ ያለው ፍቃድ፣ እሱም ምናልባት የሚናገረው በርግጥ የተከናወነውን ነው፡ እንዲህም ውሳኔው፣ ተስፋው፣ ወይም ደንቡ፣ በተለይም መለኮታዊ የሆነው፣ በተደጋጋሚ የሚነገረው በተጠናቀቀ ጊዜ ነው” ገጽ17፣ ምሳ. የተጠናቀቀ ትንቢታዊ)።

ሮበርት ቢ. ቺሾልም፣ ጁኤር. ከማብራሪያ እስከ መግለጫ፣ ይሄንን የግሥ ቅርጽ በዚህ መንገድ ይገልጸዋል፡

“...ሁኔታውን ከውጭ በኩል ይመለከተዋል፣ በጥቅሉ። ቀላል ሐቅን እንደሚገልጽ፣ ድርጊትም ቢሆን ወይም ሁኔታ (የሕላዌ ነገር ወይም የአዕምሮ)። ለድርጊቶች ጥቅም ላይ ሲውል፣ እሱ ዘወትር ድርጊትን የሚመለከተው እንደ ተጠናቀቀ ነው፣ ከአንደበተ ርቱዕነት አኳያ፣ ከተናጋሪው ወይም ከተራኪው (እሱም ቢሆንም ሆነ ባይሆንም፣ የተጠናቀቀ ሐቅ ወይም እውነታ ዋናው ነጥብ አይደለም)። የተጠናቀቀው የድርጊት/ሁኔታ ኢጋዥ ሊሆን ይችላል፣ ያለፈውን፣ የአሁኑን ወይም የወደፊቱን። ከላይ እንደተጠቀሰው፣ የጊዜ ቅምብብ፣ እሱም፣ ማንም የተጠናቀቀውን የሚተረጉምበት ላይ ተጽዕኖ የሚኖረው፣ ወደ እንግሊዝኛ መሰል፣ ጊዜ-ተኮር ቋንቋ፣ የግድ መወሰን የሚኖርበት ከዐውደ ጽሑፉ ነው” (ገጽ 86)።

ለ. ያልተጠናቀቀ፣ ይህ የሚያሳየው በእድገት ላይ ያለ ድርጊትን ነው (ያልተጠናቀቀ፣ ተደጋጋሚ፣ ቀጣይ ወይም ተያያዥነት ያለው)፣ የዘወትር እንቅስቃሴው ወደ ግቡ ነው። ይህ ቅርጽ ጥቅም ላይ የሚውለው ለአሁንና ለትንቢት ድርጊት ነው።

ጄ. ዋሽ ዋትስ፣ *በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን አገባብ ጥናት* ላይ፣ የሚለው

“ሁሉም ያልተጠናቀቁት የሚወክሉት ያልተጠናቀቀ ሁኔታን ነው። እነሱም አንድም የተደጋገሙ ወይም በእድገት ላይ ያሉ ወይም ተያያዥ የሆኑ ናቸው። በሌላ አገላለጽ፣ ወይም በከፊል እድገት ያለው፣ ወይም በከፊል የተረጋገጠ። በሁሉም ጉዳዮች እነሱ ከፊል ናቸው፣ በተወሰነ መልኩ፣ ማለትም ያልተጠናቀቀ” (ገጽ 55)።

ሮበርት ቢ. ቺሾልም፣ ጁኤር. ከማብራሪያ እስከ መግለጫ፣ የሚለው

“ያልተጠናቀቀን ጠቀሜታ በነጠላ ጽንሰ ሐሳብ ለመቀነስ አስቸጋሪ ነው፣ እሱም ሁለቱንም ገጽታዎችና ሁኔታዎች ስለሚያካልል። አንዳንድ ጊዜ ያልተጠናቀቀ ጥቅም ላይ የሚውለው በአመላካች ሁኔታ ነው እናም ተጨባጭ መግለጫ ይሰጣል። በሌላ ጊዜ እሱ አንድን ድርጊት የሚመለከተው በተያያዥነት፣ በመላምታዊ፣ በተያያዥ፣ ሊሆን በሚችል እና በመሳሰለው ነው” (ገጽ 89)።

ሐ. ተጨማሪ የሆነው ዋው፣ እሱም ግሡን ያያዘው ከፊተኛው ግሥ(ሦች) ድርጊት ጋር ነው።

መ. ተተኳሪ፣ እሱም የተመሠረተው በተናጋሪው ፍቃድ ላይ እና በሰሚው ብቃታዊ ድርጊት ላይ ነው።

ሠ. የጥንታዊ ዕብራይስጥ ትልቁ ጽሑፍ ብቻ ሥልጣናዊ የሆነ የጊዜ አስረጅዎችን ሊወስን የሚችለው።

ለ. ሰባቱ የአረባብ ቅርጾች እና የእነሱ መሠረታዊ ፍቺ። በተጨባጭ እነዚህ ቅርጾች የሚሠሩት እርስ በርሳቸው በጽሑፍ በመያያዝ ነው፣ እናም መለያየት አይኖርባቸውም።

*Qal* (kal)፣ ዋነኛው የተለመደውና መሠረታዊ የሆነ የሁሉም ቅርጾች። እሱም የሚገልጸው ቀላል ድርጊትን ወይም የመሆን ሁኔታን ነው። ምንም ዓይነት ምክንያታዊነት ወይም የተለየነት አልተደረገም።

*ኒፋል፣* ሁለተኛው በጣም የተለመደው ቅርጽ። እሱም ዘወትር ተገብሮ ነው፣ ግን ይህ ቅርጽ እንደ ተገላቢጦሽና አገናዛቢ ይሠራል። እሱም ደግሞ ምንም ምክንያታዊነት ወይም የተለየነት አልተደረገበትም።

*ፒይል፣* ይህ ቅርጽ ድርጊታዊ ሲሆን የአንድን ድርጊት ወደ ተግባር መምጣት የሚገልጽ ነው። መሠረታዊ የሆነው *የቃል* ግንድ ወደ ሕላዌ አቋም ያድጋል ወይም ይስፋፋል።

*ፑአል፣* ይህ ተገብሮ ሲሆን የፒይል ተቃርኖ አካል ነው። እሱም ዘወትር የሚገለጸው በቦዝ አንቀጽ ነው።

*ሂዝፔል፣* እሱም አገናዛቢ ወይም የተገላቢጦስ ግንድ (የግሥ) ነው። እሱም የሚገልጸው የፔል ግንድን የድርጊት ደጋጋሚነት ወይም የጊዜ መጠን ነው። አልፎ አልፎ የተገብሮ ቅርጽ *ሆዝፓል* ተብሎ ይጠራል።

*ሂፊል፣* የምክንያታዊው ግንድ የድርጊት ቅርጽ ከፔል ጋር ይቃረናል። የፈቃጅነት ገጽታ ሊኖረው ይችላል፣ ግን ዘወትር የሚያመለክተው የአንድን ሁነት ምክንያት ነው። ኤርነስት ጄኒ፣ የጀርመን ዕብራይስጥ ሰዋሰዋዊ ፣ እንደሚያምነው ፔይል አንድ ነገር ወደ መሆን እንደሚመጣ ሲገልጽ *ሂፋል* የሚያሳየው እንዴት እንደሆነ ነው።

*ሆፋል፣* ተገብሮ *የሂፋል* ተቃርኗዊ አካል ነው። እነዚህ የመጨረሻዎቹ ሁለት ግንዶች ከሰባቱ ግንዶች በአነስተኛ ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው።

አብዛኛው ይህ መረጃ የመጣው *የዕብራይስጥ ቅዱስ መጽሐፋዊ አገባብ መግቢያ*፣ በብሩስ ኬ. ዋልትኬ እና ኤም. ኦ ኮኖር፣ ገጽ 343-452 ላይ ነው።

የወኪልና የምክንያት መግለጫ። የዕብራይስጥን የግሥ ሥርዓት ለመረዳት አንደኛው ቁልፍ፣ እሱን እንደ የድምጸት ዝምድና ፈርጅ መመልከት ነው። አንዳንድ ግንዶች ከሌሎች ግንዶች ጋር ይቃረናሉ (ማለትም፣ ቃል - ኒፋል፤ ፔይል - ሂፋል)

ከታች ያለው መግለጫ የግሥ ግንዶችን መሠረታዊ ተግባር ከምክንያትነት አኳያ ለማሳየት ይሞክራል፡፡

| ድምጸት ወይም ርዕሰ ጉዳይ | ሁለተኛ ወኪል<br>የሌለው ወኪል | ንቁ ሁለተኛ<br>ሁለተኛ ወኪል | ተገብሯዊ<br>ሁለተኛ ወኪል |
|---|---|---|---|
| የድርጊት | *ቃል* | *ሂፊል* | *ፒይል* |
| መካከለኛ ተገብሮ | *ኒፋል* | *ሆፋል* | *ፑአል* |
| አገናዛቢ/የተገላቢጦሽ | *ኒፋል* | *ኒፊል* | *ሂዝፔል* |

ይህ መግለጫ የተወሰደው በጣም ጥሩ ከሆነው ማብራሪያ ከግሣዊ ሥርዓት ሲሆን፣ በአዲሱ የአካዲያን ጥናት እይታ ነው (ብሩስ ኬ. ዋልትኬ፣ ኤም. ኦ ኮነር፣ *የዕብራይስጥ ቅዱስ መጽሐፋዊ አገባብ መግቢያ*፣ ገጽ 354-359)።

አር. ኤች. ኬኒት፣ *የዕብራይስጥ ጊዜያት አጭር ሐተታ፣* አስፈላጊውን ማስጠንቀቂያ ይሰጠናል።

"በማስተማር ላይ እንዳገኘሁት፣የተማሪዎች ዋነኛ ችግራቸው በዕብራይስጥ ግሦች የሚሆነው፣ ፍችዎቻቸውን ማግኘት ነው፣ በራሳቸው በዕብራውያን አዕምሮ ውስጥ ያለውን፤ ይህም ማለት፣ ለእያንዳንዱ የዕብራይስጥ ጊዜ (የግሥ) የሆነ ቁጥር ያለው የላቲን ወይም እንግሊዝኛ ቅርጾችን የመጠቀም ዝንባሌ መኖሩ ነው፣ እኩል ይሆናል ተብሎ የሚገመተውን፣ እሱም ያ የተለየ ጊዜ ምናልባት እንደሁኔታው የሚተረጎም ይሆናል። ውጤቱም በርካቶቹን የትርጉም ድባቦች መሳት ነው፣ እሱም ሕይወትና ጥንካሬ ለብሉይ ኪዳን የሚሰጠውን።

የዕብራይስጡን ግሦች አጠቃቀም አስቸጋሪ የሚያደርገው በአንጻር ላይ ብቻ ነው፤ ስለዚህም ከእኛ ፈጽሞ ይለያል፣ እሱም ዕብራውያን አንድን ድርጊት ከሚመለከቱበት፤ ጊዜው፣ ከእኛ ጋር ያለው ቀዳሚ ግምት ውስጥ የሚገባ ነው፣ እሱም በዛው ቃል፣ 'ጊዜ' የሚያሳየው ለእነሱ እንደ ሁለተኛ ጠቀሜታ ነው። እሱም፣ የሚጠቅመው ተማሪው ጥርት አድርጎ እንዲረዳ ያደርገዋል፣ ይህም የላቲኑንም ሆነ የእንግሊዝኛውን ቅርጽ ሳይሆን፣ እነሱም እያንዳንዱን የዕብራይስጥ ጊዜ ለመተርጎም፣ ነገር ግን የእያንዳንዱ ድርጊት ገጽታ፣ ልክ በዕብራዊው አዕምሮ እንደታሰበው ባለ መልኩ።

'ጊዜያት' የሚለው ስም በዕብራይስጥ ግሦች ጥቅም ላይ ሲውል ያሳስታል። የዕብራይስጥ 'ጊዜያት' ጊዜውን የሚገልጽ አይደለም ነገር ግን የአንድን ድርጊት ሁኔታ ነው። በርግጥ እዚህጋ ለማደነጋገር አይደለም፣ 'ሁኔታ' የሚለውን ቃል በምንጠቀምበት ጊዜ፣ እሱም በስምም ሆነ በግሥ ላይ፣ 'ሁኔታዎች' ከ'ጊዜያት' በተሻለ መልኩ ያሳያሉ። ዘወትር መታሰብ ያለበት የዕብራይስጥን ግሥ አንዳች ገደብ ሳያደርጉበት ወደ እንግሊዝኛ ለመተርጎም አለመቻሉን ነው፣ (ጊዜን በተመለከተ) ይህም ሙሉ ለሙሉ በዕብራይስጥ የሌለ ነው። ጥንታዊዎቹ ዕብራውያን አንድን ድርጊት በሀላፊ ጊዜ፣ በአሁን ጊዜ፣ ወይም በትንቢት ጊዜ አያውቁትም፣ *በተጠናቀቀ* እንጂ፤ ማለትም፣ የተጠናቀቀ ወይም *ያልተጠናቀቀ* ማለትም፣ በእድገት ሂደት ላይ እንዳለ። አንድ የዕብራይስጥ ጊዜ (የግሥ) ከተጠናቀቀ፣ የሀላፊ የተጠናቀቀ፣ ወይም የእንግሊዝኛ የትንቢት ጊዜ ጋር የመሳሰሏል በምንልበት ጊዜ፣ የእሱ የዕብራውያን አስተሳሰብ፣ እንደ የተጠናቀቀ፣ የሀላፊ የተጠናቀቀ፣ ወይም የትንቢት ማለታችን አይደለም፣ ነገር ግን እንዲያው በእንግሊዝኛ ተተርጉሟል ማለታችን ነው። የአንድን ድርጊት ጊዜ ዕብራውያን በምንም ዓይነት የግሥ ቅርጽ ሊገልጹት አይሞክሩም" (መቅድም እና ገጽ 1)።

ለሁለተኛው መልካም ማስጠንቀቂያ፣ ሱ ግሩም፣ የዕብራይስጥ ቅዱስ መጽሐፋዊ ሥነ-ቋንቋ ትንታኔ፣ የሚያሳስበን፣

"ምንም ዓይነት የማወቂያ መንገድ የለውም፣ የዘመናዊ ሊቃውንት የሴማዊ መስኮችን ዳግም ግንባታ ቢሆን እንዲሁም የጥንታዊ ምውት ቋንቋዎች የአገባብ ዝምድናዎች ቢሆን፣ የራሳቸው የስሜት ነጸብራቅ፣ ወይም የገዛ ራሳቸው አፍ መፍቻ ቋንቋ፣ ወይንም ደግሞ እነዚህ መስኮች በጥንታዊ ዕብራይስጥ ይኖሩ እንደሆነ" (ገጽ 128)።

ሐ. *ሁኔታዎች* (እነዚህ ከዘመናዊ የምዕራባውያን ቋንቋዎች የተቀዱ ምስያዎች ናቸው)

እሱ ሆኗል፣ እየሆነም ነው (አመላካች)፣ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው (የተጠናቀቀ ጊዜ ወይም ቦዝ አንቀጽ (ሁሉም ቦዝ አንቀጾች አመላካች ናቸው)።

ይሆናል፣ ሊሆን ይችላል (ሁኔታ ገላጭ)

ሀ. የተመለከተ ያልተጠናቀቀ ጊዜን ይጠቀማል

ውህደት ያለው (ኤች የተጨመረበት)፣ አንደኛ መደብ ያልተጠናቀቀ እሱም በእውነቱ ፍላጎትን፣ ጥያቄን፣ በራስ መተማመንን የሚገልጽ (ማለትም፣ በተናጋሪው ፍላጎት የሆነ ድርጊት)

የግሥ ቅርጽ (ውስጣዊ ለውጥ) ሦስተኛ መደብ ያልተጠናቀቀ (ሦስተኛ መደብም ሊሆን ይችላል፣ በአሉታዊ ዓረፍተ ነገሮች) እሱም በተለምዶ የሚገልጸው ጥያቄን፣ ፍቃድን፣ ማስጠንቀቂያን፣ ወይም ምክርን ነው

ለ. የተጠናቀቀ ጊዜን ይጠቀማል *ከሉ እና ሉሊ ጋር*

እነዚህ ግንባታዎች ከሁለተኛ መደብ ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች፣ በኮኔ ግሪክ ተመሳሳይ ናቸው። የሐሰት መግለጫ (protasis ፕሮቴሲስ) የሚፈጠረው ከተሳሳተ ድምዳሜ ነው (apodosis አፖዶሲስ)።

ሐ. ያልተጠናቀቀ ጊዜንና ሉን ይጠቀማል

ይዘትና *ሉ፣* እንዲሁም የትንቢት ማሳያ፣ ይሄንን ሁኔታ ገላጭ አጠቃቀም ምልክት ያደርጋል። *ከጄ. ዋሽ ዋትስ ጥቂት* ምሳሌ፣ የዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን ሰዋሰዋዊ አገባብ ጥናት ዘፍ. 13፡6፤ዘዳ. 1፡12፤ 1ኛ *ነገሥ.* 13፡8፤ መዝ. 24፡3፤ ኢሳ. 1፡18 (ዝከ. 76-77)።

መ. *ዋው* - የተገላቢጦሽ/ተከታታይ/አገናዛቢ። ይህ የተለየ የዕብራይስጥ (ከነዓናዊ) የሰዋሰው አገባብ ለዓመታት ታላቅ ውዥንብር ፈጥሯል። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው ጽሑፋዊ-ዘውግን በተከተሉ የተለያዩ መንገዶችን በመከተል ነው። የውዥንብሩ ምክንያት የድሮ ሊቃውንት አውሮጳዊ መሆናቸውና ትርጓሜአቸውም በራሳቸው የአፍ መፍቻ ቋንቋ ቅኝት በመሆኑ ነው። ይሄም ሲረጋገጥ፣ ለችግሩ የሚጠይቁት የዕብራይስጥ "ታሳቢ" ጥንታዊ፣ የድሮውን ቋንቋ ነው። የአውሮጳ ቋንቋዎች ጊዜ (ጊዜ) ተኮር ግሦች ናቸው። አንዳንዱ ልዩነት እና ሰዋሰዋዊ አንድምታዎች የሚለዩት ዋው በሚለው ፊደል ነው፣ እሱም በተጠናቀቀው ወይም ባልተጠናቀቀ የግሥ ግንድ ላይ ነው። ይህም ድርጊቱ የታየበትን መንገድ ይቀይረዋል።

በታሪካዊ ትረካ ግሦቹ አንድ ላይ የሚያያዙት በመደበኛ ፈርጅ ባለ ሰንሰለት ነው።

የዋው ቅድመ-ቅጥያ ቀደም ሲል ከነበረው ግሥ (ሦች) የተለየ ዝምድና ያሳያል።

ትልቁ ጽሑፍ የሚሆነው ዘወትር የግሡን ሰንሰለት ለማስረዳት ቁልፍ የሆነው ነው። ሴማዊ ግሦች ተለይተው ሊተነተኑ አይችሉም።

ጄ. ዋሽ ዋትስ፣ *በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን የሰዋሰዋዊ አገባብ ቅኝት፣* የሚያስረዳው የዕብራይስጥን የዋው አጠቃቀም ከተጠናቀቀና ካልተጠናቀቀ በፊት ነው (ገጽ 52-53)። የተጠናቀቀ የሀላፊ ሐሳብ *መሠረታዊነት* እንዳለው፣ የዋው ተጨማሪነትም እሱን ዘወትር ወደ ትንቢት ጊዜ ገጽታ ያመራዋል። ይህም ደግሞ ባልተጠናቀቀውም እውነት ነው፣ እሱም *መሠረታዊ* ሐሳቡ የአሁን ወይም የትንቢት ጊዜ የሆነው፤ የዋው መጨመር ወደ ሀላፊ ያደርገዋል። ይህ ያልተለመደ የጊዜ ለውጥ ነው፣ የዋው ተጨማሪን የሚገልጸው እንጂ፣ በግሡ በራሱ ላይ የሆነ የመሠረታዊ ትርጉም ለውጥ አይደለም። የዋው የተጠናቀቁ በትንቢት ላይ በደንብ የሚሠሩ ሲሆን፣ የዋው ያልተጠናቀቁ ደግሞ ከትረካ ጋር ደኅና ይሠራሉ (ገጽ 54፣ 68)።

ዋትስ ገለጻውን ይቀጥላል፣

"በዋው መስተዋድድና በዋው ተከታታይ መካከል ላለው *መሠረታዊ* ልዩነት የሚከተሉት ትርጓሜዎች ቀርበዋል፡

*ዋው መስተዋድድ* ዘወትር የሚከሰተው ትይዩዎችን ለማመላከት ነው።

*ዋው ተከታታይ* ዘወትር የሚከሰተው ቅደም ተከተልን ለማመላከት ነው። እሱም በተከታታይ ያልተጠናቀቁ ላይ ጥቅም ላይ የዋለ ብቸኛ ቅርጽ ነው። ባልተጠናቀቁ መካከል ያለው ዝምድና በእሱ የተያያዘው ምናልባት በጊዜ ቅደም ተከተል፣ በአመክኖአዊ

(ሎጂክ) ውጤት፣ በአመክኖአዊ ሳቢያ፣ ወይም በአመክኖአዊ ተቃርኖ ነው። በሁሉም ጉዳዮች ቅድም ተከተል አለ" (ገጽ 103)።

ሠ. ያልተጠናቀቀ - ሁለት ዓይነት ያልተጠናቀቁ አሉ

ፍጹም ያልተጠናቀቀ፣ እነሱም "ጠንካራ፣ ነጻ፣ አስገራሚ ገለጻዎች እነሱም ለድራማዊ ውጤት ጥቅም ላይ የዋሉ... እንደ ባለቤት፣ እሱ የተጻፈ ግሥ የለውም፣ 'የመሆን' ግሥ፣ በርግጥ ግልጽ ነው፣ ነገር ግን ቃሉ በድራማዊ መልኩ ብቻውን ነው የቆመው፣" (ጄ. ዋሽ ዋትስ፣ *በዕብራይስጥ ብሉይ ኪዳን የሰዋሰዋዊ አገባብ ቅኝት፣"* ገጽ 92)።

ያልተጠናቀቀ አገነባብ፣ እነሱም "በሰዋሰዋዊ የሚዛመዱት በዓረፍተ ነገራቸው ከመስተዋድድ፣ አገናዛቢ ተውላጠ ስም፣ እና ያገነባብ ዝምድናዎች ጋር ነው" ገጽ 91)።

ጄ. ዌንግሪን፣ *ለጥንታዊ ዕብራይስጥ ተግባራዊ ሰዋሰው፣* ተቃርኗዊውን አቋም ይገልጻል፡

"ሁለት (ወይም ከዚያም በላይ) ቃላት በጣም በሚያያዙበት ጊዜ፣ ሁለቱ አንድ የተዋሐደ ሐሳብ ይፈጥራሉ፣ ጥገኛው ቃል (ቃላት) የሚሆነው (የሚሆኑት) በግንባታ አቋም ላይ ናቸው ይባላል" (ገጽ 44)።

ረ. ጠያቂዎች

እነሱ ዘወትር በዓረፍተ ነገር መጀመሪያ ላይ ይከሰታሉ።

ትርጓሜአዊ ጠቀሜታ

*ሀ. ሃ* - ምላሽን አይጠብቅም

*ለ. ሃሎ* - ጸሐፊው "አዎን" የሚል ምላሽን ይጠብቃል

አሉታዎች

እነሱም ዘወትር ከሚቃረኑት ቃላት በፊት ይከሰታሉ።

በጣም የታወቀው አሉታ *ሎ* ነው።

*ኣል* የሚለው ቃል ያለው ተያያዥ ፍቺ አለው፣ እሱም ጥቅም ላይ የሚውለው ከውህደታዊ እና ከግሥ ቅደም ተከተል ጋር ነው።

*ሌብሂልቲ* የሚለው ቃል፣ ፍቺው "በመሠረቱ... አይደለም፣" የሚል ሲሆን ካልተወሰኑ ጋር ጥቅም ላይ ይውላል።

*ኢን* የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የሚውለው ከቦዝ አንቀጽ ጋር ነው።

ሰ. ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች

አራት ዓይነት ሁኔታዊ ዓረፍተ ነገሮች ሲኖሩ እነሱም በመሠረቱ ከኮኔ ግሪክ ጋር ትይዩ ናቸው።

ሀ. አንድ ነገር ሊፈጸም እንደሚሆን ወይም እንደሚታሰብ አድርጎ መገመት (አንደኛ መደብ በግሪክ)

ለ. አንድ ነገር ከሐቅ ጋር የተቃረነ፣ የሱም ፍጻሜ የማይቻል (ሁለተኛ መደብ)

ሐ. አንድ ነገር የሚቻል፣ እንዲያውም ደግሞ የመሆን ዕድል ያለው (ሦስተኛ መደብ)

መ. አንድ ነገር ያነሰ የመሆን ዕድል ያለው፣ ስለዚህም፣ መፈጸሙ የሚያጠራጥር (አራተኛ መደብ)

ሰዋሰዋዊ መለያዎች

ሀ. እውነተኛ ወይም ርግጠኛ ሁኔታው ይሆናል ብሎ የሚገመተው፣ አመልካች የተጠናቀቀ ወይም ቦዝ አንቀጽ ዘወትር ሲጠቀም ነው፣ እንዲሁም ቀዳሚ ቃሉ የሚታወቀው በ

ኢም

ኪ (ወይም አሸር)

ሂን ወይም ሂኔህ

ለ. ከሐቅ ጋር የሚቃረነው ሁኔታ ዘወትር የሚጠቀመው የተጠናቀቀ ገጽታ ግሥ ወይም ቦዝ አንቀጽ እሱም ከሉ ወይም ሉሊ መቅድማዊ ቦዝ አንቀጽ ጋር ይሆናል

ሐ. በጣም የይሆናሉ ሁኔታ ዘወትር የሚጠቀመው ያልተጠናቀቀ ግሥ ወይም በቅድመ ቃሉ ያለ ቦዝ አንቀጽ ሲሆን፣ ዘወትር፣ ኢም ወይም ኪ እንደ መግቢያ ቦዝ አንቀጾች ጥቅም ላይ ይውላሉ

መ. በአነስተኛ የይሆናሉ ሁኔታ የሚጠቀመው ያልተጠናቀቀ ሁኔታ ገላጭ፣ እሱም በቅድመ ቃሉ እና ዘወትር የሚጠቀመውም ኢም እንደ መቅድማዊ አገባብ ነው፡፡

# ሐተታው ውስጥ ጥቅም ላይ የዋሉ አሕጽሮተ ቃላት

| | |
|---|---|
| መመቅ | መልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ፣ ዊሊያም ፎክስ ዌል ኦልብራይት እና ዳቪድ ኖኤል ፍሪደም ያዘጋጁት |
| መመቅመዝ.ቃ | መልሕቅ የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት (6 ቅጾች)፣ ዴቪድ ኖኤል ፍሪደም ያዘጋጀው |
| ትቁብኪ | ትንተናዊ ቁልፍ የብሉይ ኪዳን በጆን ጆሴፍ አውንስ |
| ጥቅምጽ | ጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ ጽሑፎች፣ ጀምስ ቢ. ፕሪቻርድ |
| ብድብ | እብራይስጥ እና እንግሊዝኛ ሥርወ-ቃል በብሉይ ኪዳን በኤፍ. ብራውን፣ ኤስ. አር. ድራይቨር እና ሲ. ኤ. ብሪግስ |
| ቢሄስ | ቢብላ ሄብሪካ ስቱትጋርቴንሲያ፣ ጂቢስ፣ 1997 |
| ተመዝመቅ | የተርጓሚ መዝገበ ቃላት፣ የመጽሐፍ ቅዱስ (4 ቅጾች)፣ አዘጋጅ ጆርጅ ኤ. በትሪክ |
| ዓአመመቅእ | ዓለም አቀፍ መደበኛ የመጽሐፍ ቅዱስ እንሳይክሎፔድያ (5 ቅጾች) አዘጋጅ ጀምስ ኦር |
| ኢመቅ | የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ |
| አሕማየአ | ቅዱሳት መጻሕፍት እንደ ማሶረቲክ ጽሑፍ፡ አዲስ ትርጉም (የአይሁድ የሕትመት ማኅበረሰብ የአሜሪካ) |
| ኮባ | የእብራይስና የአራማዊ ሥርወ-ቃል የብሉይ ኪዳን በሉድዊግ ኮህለር እና ዋልተር ባዉምጋርትነር |
| ላ'ም | መጽሐፍ ቅዱስ ከጥንታዊ የምስራቅ የብራና ጽሑፎች (ፓሺታ) በጆርጅ ኤም ላምሳ ሰባ ሴፕቱዋጊንት (የግሪክ እንግሊዝኛ) በ ዞንደርቫን፣ 1970 |
| ሞ'ፍ | አዲሱ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በጀምስ ሞፋት |
| ማእጽ | ማሶረቲክ እብራይስጥ ጽሑፍ |
| አአመቅ | አዲሱ የአሜሪካ መጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ |
| አአመመቅ | አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| አእመቅ | አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| አእት | አእትመጽሐፍ ቅዱስ፡ አዲሱ የእንግሊዝኛ ትርርጉም፣ ሁለተኛ ቤታ ትርጉም። |
| አዓአመቃብኪሥት | አዲሱ ዓለም አቀፍ መዝገበ ቃላት የብሉይ ኪዳን ሥነመለኮት እና ትርጓሜ (5 ቅጾች)፣ አዘጋጅ ዊሊም ኤ. ቫንጀሚረን |
| አየመመቅ | አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| አአቅ | አዲሱ ዓለም አቀፍ ቅጂ |
| አአመቅ | አዲሱ የየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ |
| ብኪምመ | የብሉይ ኪዳን የምስጋና መመሪያ በቶድ ኤስ. ቤል፣ ዊሊየም ኤ. ባንክስ እና ኮሊን ስሚዝ |
| ተእመቅ | የተከለሰ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ |
| ተመቅ | የተከለሰ መደበኛ ቅጂ |

| | |
|---|---|
| ሴፕት | ሴፕትዋጊንት (ግሪክ-እንግሊዝኛ) በዞንደርቫን፣ 1970 |
| አእቅ | የአሁን እንግሊዝኛ ቅጂ ከተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረተሰብ |
| ወጽት | የወጣቶች ጽሑፋዊ ትርጉም የመጽሐፍ ቅዱስ በሮበርት ያንግ |
| ዞስመቅእ | ዞንደርቫን ስእላዊ መጽሐፍ ቅዱስ እንሳይክሎፔድያ (5ቅጽ)፣ አዘጋጅ ሜሪል ሲ. ቴኒ |

# የጸሐፊው መልእክት፡ ይህ ሐተታ እንዴት ይረዳዎታል?

መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜ አስተውሎት እና መንፈሳዊ ሂደት ያለበት የጥንቱን ተመስጧዊ ጸሐፍት በዚህ መልኩ ከእግዚአብሔር የተቀበሉትን መልእክት በዘመናችን ለመረዳትና ለመተግበር የተዘጋጀ ነው።
መንፈሳዊ ሂደቱ ወሳኝ እና ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው። ለእግዚአብሔር መሰጠትንና ግልጽነትን ይጠይቃል።(1) ለእሱ፣ (2) እሱን ለማወቅ እና (3) እሱን ለማገልገል ጉጉትን ይፈልጋል። ይህ ሂደት ደግሞ ጸሎት፣ ንስሐ እና የሕይወትን አኗኗር ለመለወጥ ፍቃደኝነትን ይጠይቃል። በትርጓሜ ሂደት መንፈስ ወሳኝ ነው፣ ዳሩግን ትሑታንና፣ የእግዚአብሔር ሰዎች የሆኑ ክርስቲያኖች መጽሐፍ ቅዱስን በተለየ መልኩ እንደሚረዱት ምስጢር ነው።

የማስተዋሉን ሂደት ለመግለጽ ቀላል ነው። እኛ ለጽሑፉ የማናወላውልና ተገቢ ልንሆን፣ በራሳችን ወይም በእምነት ክፍላችን አስተሳሰብ ላንወሰድ ይገባል። ሁላችንም በታሪካዊ ሁኔታዎች ውስጥ ነን። ማናችንም ብንሆን ጉዳዩ የማይነካንና ገለልተኛ ተርጓሚዎች አይደለንም። ይህ ሐተታ በጥንቃቄ ማስተዋል ሂደት የተቀመረ ሦስት የትርጓሜ መርሖዎችን አዋቅሮ የያዘና አድልዎአዊ የሆኑ አስተሳሰቦቻችንን ለመቅረፍ የሚረዳ ነው።

## የመጀመሪያው መርሕ

የመጀመሪያው መርሕ የቅዱሱ መጽሐፍ ክፍል የተጻፈበትን ታሪካዊ መቼት ማጤን ነው፤ እንዲሁም የጸሐፊውም የወቅቱ ታሪካዊ ሁኔታ ይታያል። ዋነኛው ጸሐፊ ለማስተላለፍ የፈለገው ተግባርም ሆነ መልእክት አለው። ጽሑፉ ለእኛ አንዳች የሚሆን ዋነኛው፣ ጥንታዊው፣ ተመስጧዊው ጸሐፊ የጻፈው አይደለም ማለት ፈጽሞ አይደለም። የእሱ ፍላጎት የእኛ ታሪካዊ፣ ስሜታዊ፣ ባህላዊ፣ ግላዊም ሆነ ክፍለ ሃይማኖታዊ ፍላጎት ይደለም ቁልፉ ነው። ተግባር ዋነኛው ጓደኛ ነው፣ በትርጓሜ ሰዓት፣ ዳሩግን ሁልጊዜ ትክክለኛ ትርጓሜ ተግባርን መቅደም ይኖርበታል። እሱም ግሞ የሚያጠናክረው እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፍ አንድ እና አንድ ብቻ ፍቺ እንዲኖረው ነው። ይህም ፍቺ የሚሆነው ዋነኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በመንፈስ ተመርቶ በዘመኑ ሊለው የፈለገውና ሊገናኝበት ያለውን ነው። ይሄው አንዱ ፍቺ ምናልባት በርካታ አማራጭ አግባቦች ለተለያዩ ባህሎችና ሁኔታዎች ሊኖረው ይችላል። እነዚህ አገባቦች ግን ከዋነኛው ጸሐፊ ማእከላዊ እውነት ጋር የተገናኙ መሆን ይኖርባቸዋል። በዚህን ምክንያት፣ ይህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ መግቢያ እንዲሆን ነው።

## ሁለተኛው መርሕ

ሁለተኛው መርሕ ሥነ ጽሑፋዊ አሀዶችን መለየት ነው። እያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍ ሙሉ ዶሴ ነው። ተርጓሚዎች አንደኛውን የእውነት ገጽታ ሌሎች የመነጠል መብት የላቸውም። ስለሆነም እያንዳንዱን የመጽ/ፍ ቅዱስ ክፍል ከመተርጎማችን በፊት የሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ ዓላማ መረዳት ይኖርብናል። ተናጠላዊ የሆኑት ክፍሎች ማለትም ምእራፎች፣ አንቀጾች፣ ወይም ቁጥሮች ሙሉው ክፍል ያላለውን የማይሉ ላይሆኑ ይችላሉ። ርጓሜ ከሙሉ አጠቃላይ አቀራረብ ወደ ዝርዝር ክፍላዊ አቀራረብ መሆን ይኖርበታል። ስለሆነም የዚህ የጥናት መመሪያ ሐተታ የተነደፈው ተማሪዎች የእያንዳንዱን ጽሑፋዊ ክፍል በአንቀጽ በመተንተን እንዲገነዘቡት ለመርዳት ነው። የአንቀጽን ሆነ የምእራፍ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም፤ ነገር ግን የዋና ሐሳብ ክፍሎችን ለመገንዘብ ያስችሉናል። ዓረፍተ ነገርን፣ ንዑስ አንቀጽን፣ ሐረግን ወይም በቃል ደረጃ ሳይሆን በሙሉ አንቀጽ ደረጃ መተርጎም፣ የመጽሐፍ ቅዱሱን ጸሐፊ ዋነኛ ሐሳብ መረዳት ቁልፉ ነገር ነው። አንቀጾች ብዙውን ጊዜ የተመሠረቱት አንድነት ባለው ርእስ፣ ማለትም ጭብጥ ወይም መሪ ዓረፍተ ነገር በሚባለው ነው።

ያንዳንዱ ቃል፣ ሐረግ፣ ንዑስ አንቀጽ፣ እና ዓረፍተ ነገር በአንቀጹ ስጥ ያለው፣ ይብዛም ይነስም ከዋነኛው ጭብጥ ጋር ይገናኛል። ይወስኑታል፣ ስፋፉታል፣ ያብራሩታል፣ ብሎም/ወይም ይጠይቁታል። ለትክክለኛ ትርጓሜ ቁልፉ ነገር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ መከተል ሆኖ አንቀጽ በአንቀጽ ላይ በተመሠረተ አካሄድ የመጽሐፍ ቅዱሱን መጽሐፍ ባስገኙት በተናጠላዊ የጽሑፍ ክፍል በሚደረግ አግባብ ነው። ይህ የጥናት መመሪያ የሆነ ሐተታ ተዘጋጀው ተማሪዎች አዲሶቹን የእንግሊዝኛ ትርጉሞች እያነጻጸሩ እንዲያዩ ለመርዳት ጭምር ነው። እነዚህ ትርጓሜዎች ተመራጭ የሆኑበት ክንያት የተለያዩ የትርጓሜ ንድፈ-ሐሳቦችን በመጠቀማቸው ነው፡

ሀ. የተባበሩት መጽሐፍ ቅዱስ ማኅበረሰብ የግሪክ ቅጂ የተለከሰው አራተኛ እትም የተመጽማ)። ይህ ጽሑፍ በዘመናዊ የጽሑፍ ሊቃውንት አንቀጹ ተሰናድቶለታል።

ለ. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ) ቃል በቃል የተደረገ ጥሬ ርጉም ሲሆን የተመሠረተውም የግሪክ የእጅ ጽሑፍ ባህል በሆነው ቴክስተስ ሪሴፕትስ በሚባለው ነው። የአንቀጽ አደራደሩ ከሌሎቹ ትርጉሞች ረዘም ይላል። እነዚህ ረጃጅም ክፍሎች ተማሪዎች የተዋሐዱትን ርእሶች እንዲረዱ ያስችላቸዋል።

ሐ. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ትርጉም (አየተመት) ልታዊ የሆነ የቃል በቃል ትርጉም ነው። እሱም የሚከተሉት ሁለት ዘመናዊ ቅጅዎች ማእከላዊ የሆነ ነጥብ ይዟል። የአንቀጽ አደራደሩ ርእሰ ጉዳዮችን ለመገንዘብ በእጅጉን ይረዳል።

መ. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት) ዋነኛ አቻ ትርጉም ሲሆን በተባበሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ (ማኅበረሰብ) የታተመ ነው። የመጽሐፍ ቅዱሱ ትርጉም የሚሞክረውም ዘመናዊ እንግሊዝኛ አንባቢ ወይም ተናጋሪ የግሪኩን ትርጉም እንዲረዳው ማድረግ ነው። በተለይ ደግሞ የወንጌላትን አንቀጾች የሚደረድረው በርእሰ-ጉዳዩ ሳይሆን በተናጋሪው ቃል ነው የሚደረድረው፣ በአኢ ት እንደተደረገው። ተርጓሚዎች ተግባር ይሄኛው የሚረዳ አይሆንም። እዚህ ላይ ልብ ሊባል የሚገባው ሁለቱም (የተየመቅሶ) እና (የጊእት) የታተሙት በአንድ ዓይነት ሀድ ሆኖ አንቀጻቸው ይለያያል።

ሠ. የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢ. መቅ) ዋነኛው አቻ ትርጉም ሲሆን በፈረንሳይ ካቶሊክ ትርጉም ላይ ነው። የአውሮጳውያንን የአንቀጽ አደራደር ስልት ለማነጻጸር በእጅጉን ይረዳል።

ረ. በ1995 የታተመው የተሻሻለው አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ መጽሐፍ ዱስ (አአመመቅ)፣ የቃል በቃል ትርጉም ነው። ይህንን የአንቀጽ አደራደር ተከትሎም የየቁጥሩ አስተያየቶች ሰፍረዋል።

ሦስተኛው መርሕ

ሦስተኛው መርሕ ደግሞ የመጽሐፍ ቅዱስን የተለያዩ ትርጉሞችን በማንበብ ሰፋ ያለ የትርጉም አገባቦችን ማወቅ ይቻላል (በትርጉም መስክ) መጽሐፍ ቅዱስ ቃላት ወይም ሐረጎች የያዙትን። ብዙ ጊዜ የግሪክ ሐረግ ወይም ቃል በተለያየ መንገድ ነው መረዳት የሚቻለው። እነዚህ የተለያዩ ትርጉሞች እነዚህን አማራጮች በማቅረብ የተለያዩ የግሪክ አማራጭ ጽሑፎችን ለመለየት ያስችላሉ። ይህም መሠረተ እምነትን አይጸረርም፣ ዳሩግን ተመልሶ ወደ ዋናው ጽሑፍ በመውሰድ በተመስጦ የጻፈው የጥንቱ ጸሐፊ ጋ እንድንጓዝ ይረዱናል።

አራተኛው መርሕ

አራተኛው መርሕ ቃል በቃል የሆነውን ዘውግ ላማሳታወስ ነው፡፡ የመጀመሪያዎቹ ቀጥታ መልእክት የተቀበሉ ፀሐፊዎች መልእክታቸውን ለመፃፍ የተለያዩ ዘዴዎችን ይጠቀማሉ (ታሪካዊ ንግግር፣ ታሪካዊ ድራማ፣ ቅኔያዊ፣ ትንቢታዊ፣ ወንጌል ‹ምሳሌ›፣ ደብዳቤ፣ ትንቢታዊ መገለጥ) ይህ የተለያየ አፃፃፍ የተለያየ የአተረጓገም ስልት አለው፡፡ ጎርደን ፊ እና ዶጅ ሰትዋርት, *How to Read the Bible for All Its Worth*, ዲ. በረንት ሳነዴ እና ሮናልድ ሊ ጂሴ፣ ጁኦር፣ *Cracking Old Testament Codes*, ወይም ሮበርት ሰታይን, *Playing by the Rules*) ተመልከት፡፡

ይህ ሐተታ፣ ፈጠን ባለ ሁኔታ፣ ተማሪ የራሱን ትርጉሞች ይመረምር ዘንድ እንዲረዳው የታሰበ ነው። ይህም ማለት ግብ ሙሉ ለሙሉ ፍጹም ነው ማለት ሳይሆን መረጃ ሰጪ እና በጥልቀት እንድናስብ የሚያነቃቃ ነው። እርግጥ ሌሎች አማራጭ ትርጉሞችም ይረዱናል፣ አስተጋቢ፣ ቀኖናዊ፣ ወይም በመሠረተ እምነት የታጠርን እንዳንሆን። ተርጓሚዎች ሰፋ ያለ የትርጉም ዳርቻዎች እና አማራጮች ያሿቸዋል፣ የጥንቶቹ ጽሑፎች የቱን ያህል አሻሚ እንደነበሩ ለመረዳት። በጣም የሚረብሸው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ የእውነት ምንጫችን ነው የሚሉት ክርስቲያኖችም ያላቸው ስምምነት ጥቂት መሆኑ ነው።

እነዚህ መርሖዎች ብዙዎቹን ታሪካዊ ችግሮቼን እንዳሸንፍ ረድተውኛል፣ ከጥንቱ ጽሑፍ ጋር እንድተጋ በማስገደድ። እርሶንም ደግሞ ደሚባርክዎት ተስፋ አደርጋለው።

ቦብ አትሊ

ኢስት ትክሳስ ባበቲስት ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 27፣1996

# ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ መመሪያ፡ የተፈተነ እውነትን በግል ለመፈለግ

እውነትን ለማወቅ እንችላለን? የት ይገኛል? ምክንያታዊ በሆነ መንገድ ለማረጋገጥ እንችላለን? የመጨረሻ ወሳኝ ይኖር ይሆን? ሕይወታችንንም ሆነ ዓለማችንን ሊመሩ የሚችሉ የተሟሉ (ፍጹማን) ይኖራሉ? ለሕይወት ትርጉም አለው? እዚህ መሆናችን ለምድነው? የትስ እንሄዳለን? እነዚህ ጥያቄዎች፣ አስተዋይ ሰዎች የሚሰላስሏቸውና ከዘመናት መጀመሪያ አንሥቶ የሰዎችን እውቀት የሚፈትሹ ናቸው (መክ. 1፡13-18፤ 3፡9- 11)። የኔን ግላዊ ጥናት የማስታውሰው የሕይወቴ ዋነኛ ማእከል አድርጌ ነው። በየሱስ አማኝ የሆንኩት በወጣትነት ጊዜዬ ነው፤ በቅድሚያም በዋነኛነት በሌሎች የቤተሰቤ አባላት ምስክርነት። እየጎለመስኩ ስመጣ ስለራሴም ሆነ ስለ ዓለሜ ያሉኝ ጥያቄዎች እያደጉ መጡ። ተራ ባህላዊና ሃይማኖታዊ ድግግሞሾች ስለ አነበብኳቸውና ስለተረዳኋቸው የሕይወት ልምዶች፣ ትርጉም ሊሰጡ አልቻሉም። የውዥንብር ፤ የምርምር፣ የመናፈቅ እና ብዙውን ጊዜም ተስፋ የመቁረጥ ስሜት ነበር፣ በምኖርበት በድን በሆነው ደንዳና ዓለም ውስጥ።

ለእነዚህ ዋነኛ ጥያቄዎች ብዙዎች ምላሽ እንዳላቸው ይናገራሉ፣ ነገር ግን ከፍተሻ እና ከማገናዘብ በኋላ የእነሱ መልሶች የተመሠረቱት (1) በግል የሕይወት ፍልስፍናዎች፣ (2) በጥንታዊ አፈ-ታሪኮች፣ (3) በግል የሕይወት ልምዶች፣ ወይም (4) በሥነልቦናዊ ቅድመ እይታዎች ላይ ነው። በማስተዋል የሆነና ስለ ዓለም ያለኝ አመለካከት መሠረት፣ የሕይወቴ ዋነኛ ማእከል፣ የመኖሬ ዋነኛ ምክንያት ላይ ማረጋገጫ አስፈልጎኝ ነበር፣ ማስረጃ። እነዚህን መጽሐፍ ቅዱስን ሳጠና አገኘኋቸው።

ታማኝ እንዲሆንም ማስረጃ መፈለጌን ጀምሬ ያገኘሁትም፣ (1) በጥንታዊ ቅርስ ምርምር ስለ መጽሐፍ ቅዱስ የተገኘው ታሪካዊ ማረጋገጫ፣ (2) የብሉይ ኪዳን ትንቢቶች ትክክለኛለት፣ (3) በአስራ ስድስት መቶ የመጻፍ ጊዜው ውስጥ የመጽሐፍ ቅዱስ የመልእክት ኅብርና መኖር እና (4) ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር ከተገናኙ በኋላ ፍጹም የሕይወት ለውጥ ያገኙት ሰዎች የግል ምስክርነት ናቸው። ክርስትና ኅብር እንዳለው የእምነትና የሃይማኖት ሥርዓት የሰው ልጆችን ውስብስብ ጥያቄዎች የመመለስ ችሎታ አላቸው። ይህን ማድረግም የማስተዋል ውቅር ብቻ አይሰጥም፣ ነገር ግን በፍትነታዊ ገጽታው የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት የስሜት ደስታ እና መረጋጋትን ይሰጣል።

እንደማስበው፣ የሕይወቴን ዋነኛ ማእከል— ክርስቶስን በቃሉ ውስጥ አግኝቼዋለሁ። በሕይወት ልምዱ ንቁ እና ስሜት-ስሱ ነበርኩ። ቢሆንም እስካሁን ድረስ የማስታውሰው ወገግ ሊልልኝ ሲል የነበረብኝን ነውጥ እና ሥቃይ ሲሆን፣ የቱን ያህል የመጽሐፉ ትርጓሜዎች እንደሚከራከሩና፣ አልፎ አልፎም በአንድ አብያተ ክርስቲያን እና አስተምህሮዎች እንዳሉ ሳይ ነው። መጽሐፍ ቅዱስን የተመስጦ መሆንና ጠቃሚነቱን ማረጋገጥ የመጨረሻው ሳይሆን የመጀመሪያው ብቻ ነው። የተለያዩ እና ተቃርኖ ያላቸውን የመጽሐፉን ከባባድ አንቀጾች ትርጓሜዎች፣ ሁሉም ትክክለኛ እና በሥልጣን ነን እያሉ እንዴት አድርጌ እንደምቀበል ወይም እንደምተው ላውቅ እችላለሁ? ይህም ተግባር የሕይወቴ ግብ እና የእምነቴ ምናኔ ሆነ። የተረዳሁት ነገር በክርስቶስ ያለኝ እምነት፣ (1) ታላቅ ሰላምና ደስታ እንዳመጣልኝ፣ (2) የተቀናቃኝ ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች (የዓለም ሃይማኖቶች) ቀኖናዊነት፤ እና (3) የአንድ ክፍለ ሃይማኖት እብሪተኝነት እንዳለበት ተረድቻለሁ።

የጥንታዊውን ሥነ ጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ ዋጋ ያለው ፍለጋዬን ሳካሂድ ያስደነቀኝ ነገር ቢኖር የራሴን የግሌን ታሪካዊ፣ ባህላዊ፣ ክፍለ ሃይማኖታዊ እና በሕይወት ልምድ አድልዐዎች መለየት ነው። የራሴን አመለካከት ለማጠናከር መጽሐፍ ቅዱስን እንደዋዛ አዘውትሬ አነባለሁ። የራሴን ያልተሟላ ዋስትናና የብቃት ማነስ ያመላከተኝ ሌሎችን የማጠቃበት ቀኖናዊ ምንጭ አድርጌ እወስደዋለሁ። ይህንን ሀቅ መረዳት ለእኔ የቱን ያህል አስቸጋሪ ነበር! ምንም እንኳ የተሟላ ተጨባጭነት ባይኖረኝም የመጽሐፍ ቅዱስ ደኅና አንባቢ ለመሆን እችላለሁ። ያሉብኝን አድሏዊነቶች ለመለየትና እንዳሉም እውቅና በመስጠት የተወሰኑ ላደርጋቸው እችላለሁ። ከእነሱ ገና አሁንም ነጻ አይደለሁም፣ ነገር ግን ከራሴ ድክመት ተሟግቻለሁ። ተርጓሚ ዘወትር የመልካም መጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ጠላት እንደሆነ ነው! እስቲ ጥቂት ቅድመ ግምቶችን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቴ ገኘኋቸውን እርሶ አንባቢው ከእኔ ጋር ሆነው ይመረምሯቸው ዘንድ ልዘርዝራቸው፡

## ቅድመ ግምቶች

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ የሆነ የእውነተኛው አምላክ የራሱ መገለጥ መሆኑን አምናለሁ። ስለሆነም፣ መተርጎም ያለበት በዋነኛው መነሻ ብርሃን ለኮታዊ ጸሐፊ (መንፈስ) ሆኖ በተወሰነ ታሪካዊ ወቅት በነበረ ሰው ጸሐፊነት ነው።

ለ. መጽሐፍ ቅዱስ የተጻፈው ለተራ ሰዎች፣ ለሁሉም ሰዎች እንደተጻፈ አምናለሁ! እግዚአብሔር ለእኛ በግልጽ ለመናገር በታሪካዊና በባህላዊ ግባብ ራሱን አዘጋጅቶልናል። እግዚአብሔር እውነትን አይሸሽግም— እንድንረዳው ይፈልጋል! ስለሆነም በእኛ ሳይሆን በራሱ ጊዜ ብርሃን የግድ ተርጎም አለበት። መጽሐፍ ቅዱስ በመጀመሪያ ከሰሙት ወይም ካነበቡት በተለየ መንገድ የምንረዳው ማለት አይደለም። በተራ ሰው ልቦና ሊረዱት የሚችል እና ተገቢ የሆነ የሰው ልጆች መግባቢያ አግባቦችና ስልቶችን የሚጠቀም ነው።

ሐ. መጽሐፍ ቅዱስ ኅብር ያለው መልእክትና ተግባር እንዳለው አምናለሁ። ምንም እንኳ አያአዎአዊ የሆኑ አንቀጾች ቢኖሩትም ራሱን በራሱ ይቃረንም። ስለሆነም፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛው ተርጓሚ መጽሐፍ ቅዱስ ራሱ ነው።

መ. እያንዳንዱ አንቀጽ (ትንቢታትን ጨምሮ) አንድ እና አንድ ብቻ ትርጉም እንዳላቸውና ይህም በዓይነተኛው ተመስጧዊ ጸሐፊ መነሻ ሐሳብ ሆኑን አምናለሁ። ምንም እንኳ ፍጹም ርግጠኞች ባንሆንም የዓይነተኛውን ጸሐፊ ሐሳብ እንረዳዋለን፣ ብዙ ጠቋሚዎች አቅጣጫውን ስለሚያመላክቱን፡

የዘውግ (የሥነ ጽሑፋዊ) ዓይነቱ፣ መልእክቱን ለማስተላለፍ የተፈለገበት

ጽሑፉ ሊያወጣ የፈለገው እውነት ታሪካዊ ዳራ እና /ወይም የተለየ አውድ

የአጠቃላይ የመጽሐፉ ሥነ ጽሐፋዊ ሁኔታ እና እንዲሁም የእያንዳንዱ የጽሑፍ አሀድ

ጽሑፋዊ ንድፉ (ዋና ዋና ይዘቱ) ማለትም እያንዳንዱ ጽሑፍ አሀድ ከአጠቃላይ መልእክቱ ጋር ያለው ዝምድና

መልእክቱን ለማስተላለፍ የተጠቀመበት የተለየ ሰዋሰዋዊ ባሕርይ

መልእክቱን ለማቅረብ የተመረጡት ቃላት ትይዩ አንቀጾች

በእነዚህ በእያንዳንዳቸው አካባቢ የሚደረገው ጥናት በአንቀጽ ላይ የምናደርገው ጥናት ላማ ሆኗል።ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት የሚሆነውን የእኔን ዘዴ ከመግለጤ በፊት ጥቂት ተገቢ ያልሆኑ በአሁን ጊዜ ጥቅም ላይ በመዋል ላይ ያሉትንና በርካታ የተለያዩ ትርጉሞች እንዲፈጠሩ ያደረጉትና ግድ መወገድ ያለባቸውን ላመላክት፡

## II. ተገቢ ያልሆኑ ዘዴዎች


ሀ. የመጽሐፍ ቅዱስን መጻሕፍት ሥነጽሑፋዊ አውድ ችላ በማለት እያንዳንዱን ዓረፍተ ነገር፣ ሐረግ እንዲያውም ግለሰባዊ ቃላትን እንደ እውነታዊ ግለጫ፣ ከጸሐፊው ዓላማ ባልተገናኘ መልኩ ወይም ከሰፊው የጽሑፉ ክፍል ጋር ባልተያያዘ ሁኔታ መውሰድ። ይህም ዘወትር "የጽሑፍ ማጣራት" ይባላል።

ለ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት እና በግምታዊ ታሪካዊ ዳራ በመቀየር ከጽሑፉ ጋር መጠነኛ ግንኙነት ወይም ምንም ዓይነት ድጋፍ በሌላቸው ጋር ማያያዝ


ሐ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት እንደ አካባቢያዊ የጧት ጋዜጣ ዓይነት ቀድኖውኑ ለዘመናዊ ክርስቲያን እንደተጻፈ ዓይነት ማንበብ

መ. የመጻሕፍቱን ታሪካዊ አውድ ችላ በማለት ለጽሑፉ ተምሳሌታዊ ፍቺ በመስጠት ፍልስፍናዊ/ሥነ- መለኮታዊ በማድረግ በመጀመሪያ ቃሉን ከሰሙት እና ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ሐሳብ በማይገናኝ መልኩ መያዝ

ሠ. ዋነኛውን መልእክት ችላ በማለትና የራስን የሥነ-መለኮት ሥርዓት፣ አባባይ መሠረተ- እምነት፣ ወይም የወቅቱን ጉዳይ በመቀየር፣ እና ከማይገናኝ ጋር በማያያዝና፣ ዋናው ጸሐፊ ሊል ከፈለገው ቁምነገርና ከተቀመጠው መልእክት መውጣት። ይህ የአካሄድ ክስተትም ዘወትር የሚደረገው የተናጋዊውን ሐሳብ ለማጠናከር በቅድሚያ ከመጽሐፍ ቅዱስ ማንበብን ነው። ይህን ዘወትር፣ "የአንባቢ ምላሽ" ("ጽሑፉ ለእኔ የሚሰጠኝ" ትርጉም ተብሎ ይታወቃል። በሰዎች የጽሑፍ መግባቢያ ላይ ቢያንስ ሦስት አካላት ያስፈልጋሉ፡




ቀደም ሲል የተለያዩ የምንባብ ስልቶች ከሦስቱ በአንደኛው ክፍሎች አተኩረው ነበር። ነገር ግን በእውነት ለማጽናት ልዩ የሆነው የመጽሐፍ ቅዱስ መስጦ የተሻሻለው ንድፍ ይበልጥ ተገቢነት አለው።




እንደ እውነቱ ሦስቱም አካሎች በትርጓሜ ሂደት የግድ መካተት ይኖርባቸዋል። ለማረጋገጥ ያህልም የእኔ ትርጓሜ ያተኮረው በቀዳሚዎቹ በሁለቱ ካላት ላይ ነው፡ ዋነኛው ጸሐፊ እና ጽሑፉ። ምናልባት የእኔ ተቃርኖ ባስተዋልኩት ተገቢ ያልሆነ ሁኔታ ላይ ይሆናል። (1) ተምሳሌታዊ ወይም መንፈሳዊ በተደረጉ ጽሑፎች እና (2) "የአንባቢ ምላሽ" (ለእኔ የሚረዳኝ) ትርጓሜዎች። በዛባት በሁሉም ደረጃ ላይ ሊከሰት ይችላል። ዘወትር የእኛን መሻት፣ አድሏዊነት፣ አግባብ፣ እና አፈጻጸማችንን መመርመር ይኖርብናል። ምንም ዓይነት ወሰኖች ለትርጉሞች በሌሉበትን፣ ገደብና መስፈርት በሌለበት እንዴት አድርገን መፈተሽ እንችላለን? ለዚህ ነው የጸሐፊው መነሻ ሐሳብና የጽሑፉ አወቃቀር የተወሰኑ መስፈርቶችን ሰጥቶኝ ዳራውን ለመወሰንና ተገቢ የሆነ ይሁንታ ያለው ትርጓሜ እንዳደርግ ያስቻለኝ።

በእነዚህም ተገቢ ባልሆኑ ስልቶች ጭላንጭል ምን ዓይነት ታሳቢ አግባቦች ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ እና ትርጓሜ በተረጋገጠ ደረጃ የሚያመጡ እና ቋሚነት ያላቸው ሊኖሩ ይችላሉ?

## III. ለመልካም የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ተገቢ አገባቦች

በዚህ ነጥብ የተወሰኑ የትርጓሜ ዘውጎችን የተለዩ ስልቶችን አላብራራም፤ ነገር ግን ለሁሉም ዓይነት የቅዱሳን መጻሕፍት አጠቃላይ የጽሑፍ ትርጓሜ ተገቢ መርሖዎች ላይ ነው። ለተወሰነ ዘውጋዊ አግባብ መልካም የሆነው መጽሐፍ፣ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ ጠቀሜታው እንዴት እንደሚነበብ፣ በጎርዶን ፊ እና ዳግላስ ስቱአርት፣ በዞንደርቫን የታተመው ነው። የኔ ዘዴ በመነሻው ያተኮረው አንባቢ ለመንፈስ ቅዱስ መጽሐፍ ቅዱስን ያበራላቸው ዘንድ ሲፈቅዱ የሚያልፉባቸውን አራት የግል የንባብ ሀደቶችን ነው። ይህም መንፈስን፣ ጽሑፉን እና አንባቢውን ቀዳሚ ያደርጋቸዋል፣ ተከታይ ሳይሆን። ይህም ደግሞ አንባቢው በተንታኞች ሐሳብ አለቅጥ እንዳይወሰድ ያደርገዋል። ሲባል የሰማሁትም፣ "መጽሐፍ ቅዱስ እጅግ ብርሃን በሐተታዎች ላይ ያበራል" የሚል ነው። ይህም ማለት ግን የጥናት መርጃዎችን ለማንኳሰስ አይደለም፣ ነገር ግን ለአጠቃቀማቸው ተገቢ ጊዜ ማስፈለጉን ለማመላከት ነው እንጂ። ትርጓሜዎቻችንን ከቃሉ ከራሱ ለማስደገፍ መቻል ይኖርብናል።

ስድስቱ አካባቢዎች ምናልባት የተወሰኑ የእውነት ማረጋገጫ ይሰጡናል፡፡

የዋናው ጸሐፊ

ሀ. ታሪካዊ መቼት

ለ. ሥነ-ጽሑፋዊ አውድ

የዋናው ጸሐፊ ምርጫ

ሀ. ሰዋሰዋዊ መዋቅር (አገባብ)

ለ. የተመሳሳይ ሥራዎች አጠቃቀም
ሐ. የጽሑፍ ዓይነት (ዘውግ)
የእኛ ተገቢ የሆነውን የመረዳት ችሎታ
ሀ. የጊዜው ትይዩ አንቀጾች
ለ. ከአስተምህሮቶች ጋር ያለው ግንኙነት

ከትርጓሜአችን ጀርባ ምክንያቶችንና አመክኖዎችን (ሎጂክ) ማሳየት መቻል አለብን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የእምነትና የድርጊት ምንጫችን ነው። ቢያሳዝን መልኩ፣ ክርስቲያኖች በሚያስተምረው ወይም በሚያጸናው ላይ ዘወትር አይስማሙም። ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ መሆኑን ተቀብሎ ከዚያም አማኞች ለሚያስተምረውም ሆነ ለሚጠይቀው ላለመስማማት መቻል በራስ እንደመሸነፍ ነው!

አራቱ የንባብ ሀደቶች የተነደፉት የሚከተለውን ጠለቅ ያለ ትርጓሜ ለመስጠት ነው።

ሀ. የመጀመሪያው የንባቡ ኡደት

መጽሐፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ ያንብቡት። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች አገኛለሁ ብለው ተስፋ በማድረግ በድጋሚ በተለያዩ ትርጉሞች ያንብቡት

ሀ. ቃል በቃል (NKJV, NASB, NRSV)
ለ. ንቁ ቀጥተኛ TEV, JB)
ሐ. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)

የሙሉ ንባቡን ማእከላዊ ሐሳብ ይፈልጉ። ጭብጡን ይግለጡት።

የጽሑፋዊ አሀዱን (ከተቻለ) ይለዩት፤ ምእራፍ፣ አንቀጽ ወይም ዓረፍተ ነገር በትክክል ሊያብራራ የሚችለውን፣ የጭብጡን ማእከላዊ ሐሳብ ለማግኘት።

ዋነኛውን ገገር የሥነ-ጽሑፋዊ ጭብጥ ዘውግ (ዓይነት) ይግለጡት

ሀ. ብሉይ ኪዳን
ይእብራይስጥ ትረካ
የእብራይስጥ ቅኔ (መጽሐፈ- ጥበብ፣ መዝሙራት)
የእብራይስጥ ትንቢት (ስድ ንባብ፣ ቅኔ)
ሕግጋት

ለ. አዲስ ኪዳን
ተራኪ (ወንጌላት፣ ግብረ-ሐዋርያት)
ምሳሌዎች (ወንጌላት)
ደብዳቤዎች/መልእክቶች
ትንቢታዊ ሥነ-ጽሑፍ

ለ. ሁለተኛው የንባብ ሀደት

ሙሉ መጽሐፉን እንዳለ በድጋሚ ያንብቡት፣ ዋናውን ርልሰ-ጉዳይ፣ ቁም-ነገሮች ለመለየት ፈልጉ
ዋናዎቹን ርእሶች በዋና ሐሳብ ለይተው አጠር ባለ እና በቀላል መግለጫ ይዘቱን ያስቀምጡ
የድርጊት መግለጫውን ይፈትሹና ሰፋ ያለ የርእሰ ጉዳይ ዝርዝር በጥናት መርጃ ይጠቀሙ

ሐ. ሦስተኛው የንባብ ኡደት

ሙሉ መጽሐፉን በድጋሚ ያንብቡት፣ ለጽሑፉ ታሪካዊ መቼትና የተለየ አውድ ለማግኘትና ለመለየት ከራሱ ከመጽሐፍ ቅዱስ ይሞክሩ

በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱትን ታሪካዊ ዓይነቶች ይዘርዝሩ

ሀ. ጸሐፊው
ለ. ዘመኑ
ሐ. ተቀባዮች
መ. ለመጻፍ የተለየ ምክንያት
ሠ. ከመጽሐፉ ዓላማ ጋር የተያያዙ ባህላዊ መቼቶች ገጽታ
ረ. ከታሪካዊ ሰዎችና ሁነቶች የሚጠቀሱ

የምትተረጉመውን ያንን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የዋና ፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር ወደ አንቀጽ ደረጃ አስፋፉት። ዘወትር የሥነ ጽሑፉን አሀድ ለዩት፣ እንዲሁም የፍሬ ሐሳቡን ዝርዝር አውጡ። ይህም ምናልባት በርካታ ምእራፎች ወይም አንቀጾች ይሆናል። ይህም የዋናውን ጸሐፊ የሐሳብ ተገቢነት (ሎጂክ) ጽሑፋዊ ንድፍ ለመከተል ያስችልዎታል።xxi

የጥናት መረጃዎችን በመጠቀም የርሶን ታሪካዊ መቼት ይፈትሹ።

መ. አራተኛው የንባብ ሀደት

የተለየውን የጽሑፍ ክፍል በልዩ ልዩ ትርጉሞች ያንብቡት

ሀ. ቃል በቃል (አኪጀት፣ አአሰመቅ፣ አየተመት)
ለ. ንቁ አቻ (የአእቅ፣ 1መቅ)
ሐ. ማብራሪያ (ሕያው ቃል፣ የተብራራ መጽሐፍ ቅዱስ)

ሥነ-ጽሑፋዊ ወይም ሰዋሰዋዊ መዋቅሮችን ይፈልጉ

ሀ. ተደጋጋሚ ሐረጎች፣ ኤፌ. 1፡6፤12፤13

ለ. ተደጋጋሚ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች፣ ሮሜ. 8፡31
ሐ. ተጻጻራሪ ጽንሰ-ሐሳቦች

የሚከተሉትን ዓይነቶች ይመዝግቡ

ሀ. ወሳኝ ቃላት
ለ. ያልተለመዱ ቃላት
ሐ. ዋነኞቹ ሰዋሰዋዊ መዋቅሮች
መ. የተለዩ አስቸጋሪ ቃላት፣ ሐረጎች፣ እና ዓረፍተ ነገሮች

ዋነኞቹን ትይዩ አንቀጾች ይለዩ

ሀ. ከርእሰ ጉዳዩ ጋር በጣም ግልጽ የሆነውን የማስተማሪያ አንቀጽ ይፈልጉ
"ስልታዊ ሥነ-መለኮት" መጻሕፍት
የማጣቀሻ መጽሐፍ ቅዱስ
የቃላት ዝርዝር

ለ. በርእሰ ሐሳብህ ዙሪያ ተስማሚ አያዎአዊ ጥንዶችን ከጽሑፉ ይፈልጉ። አብዛኞቹ የቅዱሳት መጻሕፍት እውነታዎች ሚቀርቡት በአከራካሪ ጥንዶች ነው፤ በርካታ የመሠረተ እምነት ግጭቶች የሚመነጩት ከጽሑፍ አቃቂር ማውጣት ለትም ከፊል ከሆነ የመጽሐፍ ቅዱስ ክርክሮች ነው። መላው መጽሐፍ ቅዱስ ተመስጧዊ ነው፣ እኛም የተሟላውን መልእክት በመፈለግ፣ የመጽሐፍ ቅዱስን ሚዛን በትርጓሜአችን መጠበቅ ይኖርብናል።

ሐ. በዛው በመጽሐፉ ውስጥ ፣ በዛው ጸሐፊ ወይም በዛው የሥነ ጽሑፍ ዓይነት፣ አቻዊ ትይዩ ይፈልጉ፤ መጽሐፍ ቅዱስ የራሱ ምርጥ ተርጓሚ ነው፤ ምክንያቱም፣ አንድ ብቸኛ ጸሐፊ ስላለው— መንፈስ ቅዱስ።

ታሪካዊ መቼቱንና የተለየ አውዱን ለመፈተሽና ለማስተዋል የጥናት መረጃዎችን ይጠቀሙ።

ሀ. የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ
ለ. የመጽሐፍ ቅዱስ አውደ-ጥበባት፣ መምሪያ መጻሕፍ እና መዝገበ ቃላት
ሐ. የመጽሐፍ ቅዱስ መግቢያዎች
መ. የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታዎች (በዚህ ነጥብ ላይ በጥናትዎ፣ አማኝ የኅብረተሰብ ክፍሎችን፣ ለትም የቀደምቱም ሆኑ ያሁኖቹ የራስዎን ጥናት ለማገዝና ለማረም ይጠቀሙባቸው።)

# IV. የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ አተገባበር

በዚህ ነጥብ ወደ አተገባበር እንቃኛለን። ጽሑፉን ከዋናው መቼት አንጻር ለመረዳት ጊዜ ወስደዋል፤ አሁን ደግሞ ይሄንኑ በሕይወትዎ፣ በባህልዎ ተገብሩት ይገባል። የመጽሐፍ ቅዱስ የመረዳት ሥልጣን ማለት በእኔ አገላለጽ፣ "ዋናው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊ በእሱ ጊዜ ሊለው የፈለገውን መረዳትና ያንን በራሳችን ጊዜ መተርበር" ማለት ነው። ድርጊት መከተል ያለበት የዋናውን ጸሐፊ የትርጓሜ ሐሳብ በጊዜም ሆነ በሎጂክ አኳያ ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን አንቀጽ በጊዜው ምን ለማለት እንደፈለገ እስካላወቅን ድረስ በዘመናችን ልንተገብረው አንችልም! የመጽሐፍ ቅዱስ አንቀጽ ለው ያልፈለገውን ፈጽሞ ሊሆን አይችልም! የእርስዎ የተዘረዘረ የዋና ሐሳቦች ዝርዝር በአንቀጽ ደረጃ (የንባብ ሀደት ቁጥር 3)፣ የእርስዎ መመሪያ ይሆናል። ትግበራ መደረግ ያለበት በአንቀጽ ደረጃ እንጂ በቃላት ደረጃ መሆን የለበትም። ቃላት ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ሐረጎች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው፤ ዓረፍተ ነገሮች ትርጉም የሚኖራቸው በከፊለ- ጽሑፍ ደረጃ ነው።

ብቸኛው ተመስጧዊ ሰው በትርጓሜው ሂደት ውስጥ ዋነኛ ጸሐፊው ነው። በመንፈስ ቅዱስ አብራሪነት (ማብራሪያ) የእሱን ምሪት ብቻ መከተል ይኖርብናል። ማብራሪያ ግን ተመስጦ ማለት አይደለም። "እግዚአብሔር እንደዚህ ይላል፣" ለማለት ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር የግድ መኖር አለበት። ትግበራ በተለይ መያያዝ ያለበት በሙሉ መጽሐፉ ሐሳብ ላይ ሲሆን፣ የተለየው የጽሑፍ አሀድ እና በአንቀጽ ደረጃ እያደገ በሚሄድ መልኩ። የዘመናችን ጉዳዮች መጽሐፍ ቅዱስን እንዲተረጉሙ አትፍቀዱ፤ መጽሐፍ ቅዱስ ይናገር! ይህ ምናልባት የተወሰኑ ከጽሑፉ እንድናወጣ ይጠይቀን ይሆናል። ይህም ተገቢ የሚሆነው ጽሑፉ ለመርሖቹ ድጋፍ ሲሆን ነው። በሚያሳዝን መልኩ ግን፣ ብዙውን ጊዜ የእኛ መርሖዎች፣ "የእኛ" መርሖዎች ናቸው— የጽሑፉ መርሕ በመሆን ፈንታ።

መጽሐፍ ቅዱስን ለመተግበር፣ (ከትንቢት ብቻ በቀር) ማስታወስ የሚገባን ጠቃሚ ነገር ለእያንዳንዱ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አንድና አንድ ብቻ ርጉም እንዳለው ነው። ያም ትርጉም ግንኙነቱ ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ጋር፣ እሱም የዘመኑን ውድቀትም ሆነ ፍላጎት እንዴት እንዳቀረበው ነው። በርካታ ተስማሚ ድርጊቶች ከዚህ ከአንዱ ትርጉም ሊመነጩ ይችላሉ። አተገባበሩም የሚመሠረተው በተቀባዮቹ መሻት ላይ ሆኖ፣ መገናኘት ያለበት ግን ከዋናው ጸሐፊ ሐሳብ ላይ ነው።

# V. የትርጓሜ መንፈሳዊ ገጽታዎች

እስካሁን አመክኖአዊ የሆነ እና የሥነ ጽሑፋዊ ሂደት በምን መልኩ በትርጉምና በአተገባበር ላይ መሆን እንዳለበት ለማብራራት ሞክሬአለሁ። አሁን ደግሞ ስለ ትርጉም መንፈሳዊ ገጽታ በአጭሩ ላብራራ። የሚከተሉት የመቆጣጠሪያ ዝርዝሮች ረድተውኛል፡

ሀ. ለመንፈስ ርዳታ ይጸልዩ (1ኛ ቆሮ. 1፡26-2፡16)።
ለ. ከሚታወቅ ኃጢአት በግልዎ ምሕረትንና መንጻትን እንዲያገኙ ይጸልዩ (1ኛ ዮሐንስ 1፡9)።
ሐ. ስለ እግዚአብሔር ለማወቅ ከፍተኛ ፍላጎት እንዲያድርብዎ ይጸልዩ (መዝ. 19፡7-14፤ 42፡1፤ 119፡1)።
መ. አዲስ ማስተዋልን በሕይወትዎ ወዲያውኑ ይተግብሩ።
ሠ. ትሑትና ለመማር የተዘጋጁ ይሁኑ።

በሎጂካዊ ሂደት እና በመንፈስ ቅዱስ መንፈሳዊ መሪነት መካከል ያለውን ሚዛን ለመጠበቅ በጣም አዳጋች ነው። የሁለቱን ሚዛን ለመጠበቅ የሚከተሉት ጥቅሶች ረድተውኛል፡

ሀ. ከ ጀምስ ደብሊዩ. ሲር፣ *ቃሉን መጠምዘዝ* (ማጣመም) ገጽ 17-18

“ማብራሪያ የሚመጣው ወደ እግዚአብሔር ሕዝቦች ሐሳብ ነው— ወደ መንፈሳዊ ምሑር ሳይሆን።በመጽሐፍ ቅዱስ ክርስትና የተለየ የመማሪያ ክፍል የለም፣ ምንም የተለየ የሚያብራራ፣ ተገቢው ትርጓሜ የሚመጣላቸው የተለዩ ሰዎች የሉም። እና ስለዚህ፣ መንፈስ ቅዱስ ልዩ የጥበብ፣ እውቀት፣ እና መንፈስን የመለየት ጸጋ ሲሰጥ፣ እነዚህ ባለጸጋ ክርስቲያኖች ብቻ የቃሉ ሥልጣናዊ ተርጓሚዎች እንዲሆኑ መመደቡ አይደለም። ሁሉም የራሱ ሕዝቦች ሊማሩ፣ ሊዳኙ እና ሊለዩ፣ በእነሱ፣ እግዚአብሔር የተለየ ችሎታ ለሰጣቸው እንኳ ሥልጣን ያለውን መጽሐፍ ቅዱስ መጥቀስ እንደሚችሉ ነው። ለማጠቃለል፣ በሙሉው መጽሐፍ ያቀረብኩት ሐሳቤ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛው የእግዚአብሔር መገለጥ ለሰው ልጆች ሁሉ ነው፣ በሚናገረው ሁሉ የመጨረሻው ባለሥልጣን ነው፤ በጥቅሉ ምሥጢራዊ ሳይሆን በማንኛው ባህል ባሉ ተራ ሰዎች በበቂ መልኩ ለመረዳት የሚቻል ነው።”

ለ. በኬርክጋርድ፣ በቤርናንድ ራም በሚገኘው፣ የፕሮቴስታንት የቅዱሳት መጻሕፍት ትርጓሜ፣ ገጽ 75፡
እንደ ኬርክጋርድ ከሆነ ሰዋሰዋዊ፣ ቃላዊ፣ እና ታሪካዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናቶች አስፈላጊ ናቸው፤ መቅደም ያለበት ግን የመጽሐፍ ቅዱስ ልባዊ ንባብ ነው። “መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ለማንበብ፣ ማንም አፍ ከልብ ሆኖ፣ በተጠንቀቀ ሆኖ፣ በጉጉትና ተስፋ በማድረግ፣ ከእግዚአብሔር ጋር እየተነጋገረ ማንበብ አለበት። መጽሐፍ ቅዱስን በሐሳበ ቢስነት ወይም በግዴለሽነት ወይም እንደ ትምህርት ወይም እንደ ልዩ ሞያ ማንበብ መጽሐፍ ቅዱስን እንደ እግዚአብሔር ቃል ማንበብ አይደለም። አንዱ የፍቅር ደብዳቤ እንደሚነበብ የሚያነበው ከሆነ እሱ እንደ እግዚአብሔር ቃል እያነበበው ነው።”

ሐ. ኤች. ኤች. ሮውሊ *በየመጽሐፍ ቅዱስ ጠቀሜታ፣* ገጽ 19፡
“የተሻለ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሑራዊ መረዳት፣ ምንም ያህል ፍጹም ቢሆን ሁሉንም ሀብቶች ሊያስገኝ አይችልም። ይህን መሰሉን መረዳት ዝቅ ለማድረግ አይደለም፣ ለፍጹም መረዳት አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ፍጹም ይሆን ዘንድ ወደ መጽሐፉ መንፈሳዊ ሀብቶች የሚያመራ መንፈሳዊ መረዳት ማስፈለጉን ለማሳየት ነው። እናም ለዛ መንፈሳዊ መረዳት ከምሑራዊ ንቁነት የተሻለ ነገር ያስፈልጋል። መንፈሳዊ ነገሮች በመንፈሳዊነት የሚለዩ ናቸው፤ እናም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የመንፈሳዊ ተቀባይነት አዝማሚያ ሊኖረው ይገባል፣ ራሱን ይሰጥ ዘንድ እግዚአብሔርን ለመፈለግ ጉጉት ያለው፣ ከሳይንሳዊ ጥናቱ ባሻገር ወደ ተትረፈረፈ ሀብት ወራሽነት ወደሚያስገኝ ወደዚህ ከመጻሕፍት ሁሉ ታላቅ ወደ ሆነ።”

## VI. የሐተታው ዘዴ

የጥናት መመሪያ ሐተታው የተሰናዳው የእርስዎን የትርጉም አግባብ በሚከተሉት መንገዶች ለማገዝ ነው፡

ሀ. እያንዳንዱን መጽሐፍ የሚያስተዋውቅ አጭር ታሪካዊ የዋና ሐሳብ መግለጫ። “የንባብ ሀደት ቁጥር 3” ካነበበቡ በኋላ ይህን መረጃ ያረጋግጡት።

ለ. ጽሑፋዊ ማብራሪያዎች በየአንዳንዱ ምእራፍ መጀመሪያ ላይ ይገኛል። ይህም ሥነ ጽሑፋዊ አሀዱ እንዴት እንደተዋቀረ ለመመልከት ይረዳል።

ሐ. በእያንዳንዱ ምእራፍ ወይም ሥነ ጽሑፋዊ አሀድ፣ የአንቀጽ ክፍሎች እና መግለጫ ጽሑፎች ከተለያዩ በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች ተሰጥተዋል፡

የመጽሐፍ ቅዱስ ኅብረት ሶሳይቲ የግሪክ ጽሑፍ፣ አራተኛ እትም (የተመቅሶ)

አዲሱ የአሜሪካ መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ፣ 1995 የተሻሻለ (አአመመቅ)

አዲሱ ኪንግ ጀምስ እትም (አኪጀእ)

አዲሱ የተከለሰው መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አየመመቅ)

አዲሱ የእንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አእመቅ)

የኢሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ)

የአንቀጽ ክፍሎች ተመስጧዊ አይደሉም። ከጽሑፉ መረጋገጥ ይኖርባቸዋል። ከተለያዩ የትርጉም ንድፈ ሐሳቦች እና ሥነመለኮታዊ አስተሳሰቦች የተለያዩ ዘመናዊ ትርጉሞችን በማወዳደር የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን ለመተንተን እንችላለን። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ዋነኛ እውነት ይዟል። ይህም “መሪ ዓረፍተ ነገር” ወይም “የጽሑፉ ማእከላዊ ሐሳብ” ተብሎ ይጠራል። ይህም ኅብር ያለው ሐሳብ አግባብነት ላለው ታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊ ርጉም ቁልፉ ነው። ማንም ከአንድ አንቀጽ ባነሰ መተርጎም፣ መስበክ ወይም ማስተማር ይኖርበትም! በተጨማሪም እያንዳንዱ አንቀጽ ከአካባቢው አንቀጾች ጋር እንደሚዛመድ አስታውሱ። ለዚህ ነው በአንቀጽ ደረጃ ያለ የዋና ሐሳቦች ርዝር ለሙሉ መጽሐፉ በጣም አስፈላጊ የሆነው። በዋናው ተመስጧዊ ጸሐፊ የተገለጠውን ርእሰ ጉዳይ አመክኖአዊ ፍሰት መከተል መቻል ኖርብናል።

መ. የቦብ ማስታወሻዎች በትርጓሜ የሚከተሉት ቁጥር በቁጥር የሆነውን አግባብ ነው። ይህም የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ እንድንከተል ያስገድደናል። ማስታወሻዎቹ ከብዙ አካባቢዎች መረጃዎችን ይሰጡናል።

ሀ. ሥነ ጽሑፋዊ ተጓዳኝ ጽሑፍ

ለ. ታሪካዊ፣ ባህላዊ መረዳቶች

ሐ. ሰዋሰዋዊ መረጃ

መ. የቃላት ጥናቶች

ሠ. ጠቃሚ ትይዩ አንቀጾች

ሠ. በተወሰኑ ነጥቦች በሐተታው ውስጥ፣ አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ ትርጉም (በ1995 የተሻሻለ) የኅትመትጽሑፍ፣ ከሌሎች በርካታ ዘመናዊ ትርጉሞች በደጋፊነት ይኖራሉ፡

ሀ. አዲሱ የኪንግ ጀምስ ቅጂ (አኪጀቅ)፣ የጽሑፋዊ እጅ ጽሑፎችን ማለት “ቴክስተስ ሪሴፕተስ” የሚከተል ነው።

ለ. አዲሱ የተከለሰው መደበኛ ቅጂ (አየተመቅ)፣ ማለትም ቃል በቃል የሆነ ትርጉም ሲሆን፣ እሱም የተከለሰው መደበኛ ትርጉም ከቤተክርስቲያን ብሔራዊ ምክር ቤት ነው።
ሐ. የጊዜው እንግሊዝኛ ትርጉም (የጊእት)፣ ከአሜሪካን የመጽሐፍ ቅዱስ ሶሳይቲ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ነው።
መ. የየየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ነመቅ)፣ ከፈረንሳይ ካቶሊክ የተሻሻለ አቻ ትርጉም ላይ የተመሠረተ የእንግሊዝኛ ትርጉም ነው።

ረ. ግሪክኛን ለማያነቡ፣ ተነጻጻሪ እንግሊዝኛ ትርጉሞች በጽሑፉ ውስጥ ያሉትን አስቸጋሪ ክፍሎች ለመረዳት ይጠቅማሉ፡
ሀ. የእጅ ጽሑፍ ልዩነቶች
ለ. አማራጭ የቃላት ፍቺዎች
ሐ. ሰዋሰዋዊ አስቸጋሪ ጽሑፎችና አወቃቀሮች
መ. አሻሚ ጽሑፎች የእንግሊዝኛ ትርጉም እነዚህን ችግሮች ባያቃልልም እንኳ፣ ጠለቅ እና ውስጣዊ የሆነ ጥናት ይደረግ ዘንድ አላማና ስፍራውን ያሳያሉ።

ሸ. በእያንዳንዱ ምእራፍ መዝጊያ ላይ ጠቃሚ የውይይት ጥያቄዎች ተሰጥተዋል፣ እነዚህም የምእራፉን ዋነኞቹን የትርጓሜ ጉዳዮች ነላማ ለማድረግ የሚሞክሩ።

# የዕብራይስጥ ቅኔ መግቢያ

መግቢያ

ሀ. ይህ ዓይነቱ ሥነ-ጽሑፍ የብሉዩ ኪዳንን እስከ 1/3ኛ ይደርሳል። እሱም በተለይ "ነቢያት" ላይ የተለመደ ነው (ከሐጌና ከሚልክያስ በቀር ሁሉም ቅኔ ይዘዋል) እናም የዕብራይስጥ ካኖን (ቅዱሳት መጻሕፍት) "የጽሑፍ" ክፍሎች።

ለ. እሱም ከእንግሊዝኛ ቅኔ እጅግ ይለያል። የእንግሊዝኛ ቅኔ የዳበረው ከግሪክና ከላቲን ቅኔ ነው፣ እሱም በቀዳሚነት በድምጽ ላይ የተመሠረተ። የዕብራይስጥ ቅኔ ከከነአን ቅኔ ጋር ብዙ የሚጋራው አለ። ምንም ዓይነት ማጥበቂያ ስንኞች ወይም ዜማ በቅርብ ምስራቅ ቅኔ ላይ አይገኝም (ነገር ግን ምት አለ)።

ሐ. የጥንታዊ ቅርስ ግኝት፣ በሰሜን እስራኤል ዑጋሪት ላይ (ራስ ሻምራ) ሊቃውንትን ረድቷቸዋል፣ የብኪን ቅኔ ይረዱ ዘንድ። ይህ ቅኔ፣ ከ15ኛው ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ የሆነ ግልጽ የሆነ ጽሑፋዊ ግንኙነት ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር አለው።

የቅኔ አጠቃላይ ባሕርይ

ሀ. እጅግ እምቅ ነው

ለ. እሱም እውነትን፣ ስሜትን ወይም ልምምዶችን በምናብ ለመግለጽ ይሞክራል።

ሐ. እሱም በቀዳሚነት ጽሑፋዊ ነበር፣ የቃል ሳይሆን። እሱ እጅግ መዋቅራዊ ነው። ይህም መዋቅር የሚገለጸው
ተመዛዛኝ ስንኞች (ትይዩአዊነት)
የቃላት ጨዋታ
የድምጽ ጨዋታ

መዋቅር (አር.ኬ. ሀሪሰን፣ የብሉይ ኪዳን መግቢያ፣ ገጽ 965-975)

ሀ. ቢሾፕ ሮበርት ሎውዝ በመጽሐፉ ላይ፣ የዕብራይስጥ ቅዱስ ቅኔ ትምህርት (1753) ቀዳሚው ነበር፣ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅኔ ባሕርይን እንደ ተመዛዛኝ ስንኛዊ ሐሳቦች በማድረግ። አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች የተቀረጹት የቅኔን ስንኞች ለማሳየት ነው።
ተመሳሳይ — ስንኞቹ ተመሳሳይ ሐሳብን በተለያዩ ቃላት ይገልጻሉ፡
ሀ. መዝሙር 3:1፤ 49:1፤ 83:14፤ 103:13
ለ. ምሳሌ 19:5፤ 20:1
ሐ. ኢሳይያስ 1:3፣10
መ. አሞጽ 5:24፤ 8:10
ተቃራኒ — ስንኞቹ ተቃራኒ ሐሳቦችን ይገልጻሉ፣ በማቃረን መልኩ ወይም አዎንታዊና አሉታዊውን በማስቀመጥ፡
ሀ. መዝሙር 1:6፤ 90:6
ለ. ምሳሌ 1:29፤ 10:1፣12፤ 15:1፤ 19:4
ድብልቅ – ቀጣዮቹ ሁለት ወይም ሦስት ስንኞች ሐሳቡን ያጎለብታሉ - መዝ. 1:1-2፤ 19:7-9፤ 29:1-2
የተመሳቀለ — የቅኔ ዘርፍ መልእክቱን ወደ ታችና ወደ ላይ በሆነ መልኩ የሚገልጽ። ዋናው ነጥብ የሚገኘው በፈርጁ መካከል ላይ ነው።

ለ. ኤ. ብሪጅስ በመጽሐፉ ላይ፣ *የቅዱስ ቃሉ ጥናት አጠቃላይ መግቢያ* (1899) የዕብራይስጥን ቅኔ ትንተና ቀጣዩን ደረጃዎች አዳብሯል፡
ተምሳሌታዊ — አንደኛው ሐረግ ጥሬአዊ እና ሁለተኛው ዘይቤአዊ፣ መዝ. 42:1፤ 103:3።
ጡዘታዊ ወይም መወጣጫ-መሰል — ሐረጋቱ እውነትን የሚገልጹት ከፍ እያለ በሚሄድ መልኩ ነው፣ መዝ. 19:7-14፤ 29:1-2፤ 103:20-22።
ወደ ውስጥ የታጠፈ — ተለጣጣቂ ሐረጋት፣ አዘውትሮም አራት የሆነ፣ በሐረጉ ውስጣዊ መዋቅር 1 ከ4 እና 2ከ3 ጋር የሚዛመድ፣ መዝ. 30፡8-10ሀ

ሐ. ጂ. ቢ. ግሬይ በመጽሐፉ ላይ፣ *የዕብራይስጥ ቅኔ መልኮች* (1915) የተመዛዛኝ ሐረጋትን ጽንጸ-ሐሳብን አዳብሯል፡
ፍጹም ሚዛናዊ — እያንዳንዱ በአንደኛው ሐረግ ላይ ያለ ቃል በሁለተኛው ሐረግ ላይ ተደግሟል ወይም ተመዛዝኗል — መዝ. 83፡14 እና ኢሳ. 1፡3
ያልተሟላ ሚዛናዊ፣ ሐረጎቹ ተመሳሳይ ርዝመት ሳይኖራቸው፣ መዝ. 59:16፤ 75:6

መ. ዛሬ እያደገ የመጣ ለዕብራይስጥ ጽሑፋዊ መዋቅር ፈርጅ እውቅና የመስጠት ሁኔታ አለ፣ መስቀልያ ተብሎ የሚጠራ፣ እሱም የትይዩ ስንኞችን ጎዶሎ ቁጥር የሚጠራ፣ የአሸዋ ብርጭቅ ቅርጽ የመሰለ፣ ለማዕከላዊው ስንኝ አጽንዖት የሚሰጥ።

ሠ. በሁሉም ቅኔዎች የሚገኘው የድምጽ ፈርጅ ዓይነት፣ ነገር ግን ዘወትር በምስራቅ ቅኔ ላይ የማይገኝ
በሆሄያት ላይ የሚጫወት (የቃላት ዕንቆቅልሽ፣ መዝሙር 9፤ 34፤ 37፤ 119፤ ምሳ. 31:10፤ ሰቆቃወ 1-4)
በተናባቢዎች ላይ የሚጫወት (ደጊመ-ቃል የተናባቢዎች፣ መዝ. 6:8፤ 27:7፤ 122:6፤ ኢሳ. 1:18-26)
በአናባቢዎች ላይ የሚጫወት (ደጊመ-ቃል የአናባቢዎች ዘፍ. 49:17፤ ዘጸ. 14:14፤ ሕዝ. 27:27)
ተመሳሳይ ድምጽ ያላቸውን ቃላት የሚጫወት፣ በተለያዩ ፍችዎች (አስቂኝ የቃላት ጨዋታ)

በሚባሉበት ጊዜ እንደ ነገሩ ስም ዓይነት በሆኑ ቃላት ጨዋታ (ድምጸ-ቀድ)
የተለየ መከፈቻ እና መዝጊያ (አካታች)

ረ. በርካታ ዓይነት ቅኔዎች በብሉይ ኪዳን ይገኛሉ። አንዳንዶቹ ርዕስ-ዘመድ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ቅርጽ-ዘመድ ናቸው፡
የምርቃት መዝሙሮች – ዘኁ. 21:17-18
የሥራ መዝሙሮች – (መሳ. 9:27 ላይ ተጠቅሰዋል፣ ነገር ግን አልተመዘገቡም)፤ ኢሳ. 16:10፤ ኤር. 25:30፤ 48:33
ባላድ (ረጅም የጀግና መዝሙሮች) – ዘኁ. 21:27-30፤ ኢሳ. 23:16
የመጠጥ መዝሙሮች (ማኅሌተ-ገንቦ) – አሉታዊ፣ ኢሳ. 5:11-13፤ አሞጽ 6:4-7 እና አዎንታዊ ኢሳ. 22:13
የፍቅር ግጥሞች – ማኅልየ ማኅልይ፣ የሰርግ ዕንቆቅልሽ – መሳ. 14:10-18፣ የሰርግ መዝሙሮች – መዝሙር 45
ሙሾ/እንጉርጉሮ – (2 ሳሙ. 1:17 እና 2 ዜና. 35:25፤ 2 ሳሙ. 3:33፤ መዝሙር 27፤ 28፤ ኤር. 9:17-22፤ ሰቆቃወ፤ ሕዝ. 19:1-14፤ 26:17-18፤ ናሆ. 3:15-19) ላይ ተጠቅሰዋል፣ ነገር ግን አልተመዘገቡም
የጦርነት መዝሙሮች – ዘፍ. 4:23-24፤ ዘጸ. 15:1-18፣20፤ ዘኁ. 10:35-36፤ 21:14-15፤ ኢያ. 10:13፤ መሳ. 5:1-31፤ 11:34፤ 1 ሳሙ. 18:6፤ 2 ሳሙ. 1:18፤ ኢሳ. 47:1-15፤ 37:21
ለመሪ የተለየ ምርቃት ወይም ባርኮት – ዘፍጥረት 49፤ ዘኁ. 6:24-26፤ ዘዳግም 32፤ 2 ሳሙ. 23:1-7
አስማታዊ ጽሑፎች – በለዓም፣ ዘኁ. 24:3-9
ቅዱስ ግጥሞች – መዝሙራት
ዕንቆቅልሻዊ ግጥሞች – መዝሙር 9፤ 34፤ 37፤ 119፤ ምሳ. 31:10 እና ሰቆቃወ 1-4
ርግማን – ዘኁ. 21:22-30
ነቀፌታዊ ግጥሞች – ኢሳ. 14:1-22፤ 47:1-15፤ ሕዝ. 28:1-23
የጦርነት ግጥሞች መጽሐፍ (Jashar ያሻር) – ዘኁ. 21:14-15፤ ኢያ. 10:12-13፤ 2 ሳሙ. 1:18

የዕብራይስጥ ቅኔን ለመተርጎም መመሪያ

ሀ. የአንጓውን ወይም የክፍሉን ማዕከላዊ እውነት ፈልግ (ይህም የስድ-ንባብ አንቀጽ የሚመስል ነው።) የተመት የመጀመሪያው ዘመናዊ ትርጉም ነው ቅኔን በአንጓ በመለየት። ዘመናዊዎቹን ትርጉሞች ለይዘት ኢጋዥነት አወዳድራቸው።

ለ. ዘይቤአዊ ቋንቋውን ለይ እና በስድ-ንባብ ግለጸው። ይህን መሰሉ ሥነ-ጽሑፍ እጅግ እምቅ እንደሆነ አስታውስ፣ ብዙ ነገሮች በአንባቢው ይሞሉ ዘንድ ተትቷል።

ሐ. ረጅም ጉዳይ-ተኮር ግጥሞችን ከዐውደ-ጽሑፋቸው ጋር ማዛመድህን ርግጠኛ ሁን (ዘወትር ሙሉው መጽሐፍ) እና ታሪካዊ መቼት።

መ. የተካተቱትን ትይዩ ዓይነቶች ለመለየት ሞክር፣ ተመሳሳይ ቢሆኑ፣ ተቃራኒ፣ ወይም ድብልቅ። ይህ እጅግ ጠቃሚ ነው።

መሳፍንት 4 እና 5 እጅግ ረጂ ናቸው ቅኔ እንዴት ታሪክን እንደሚገልጽ ለማየት። መሳፍንት 4 ስድ ንባብ ሲሆን መሳፍንት 5 ቅኔ ነው፣ የተመሳሳይ ሁነት (ደግሞም ዘዳግም 14 እና 15ን አነጻጽር)።

# የመዝሙር መግቢያ*

*አብዛኛው የዚህ ነገር የመጣው ከአር. ኬ. *የብሉይ ኪዳን መግቢያ* ገጽ 976-1003 እና ላሶር፣ ሁባርድ፣ እና ቡሽ፣ *የብሉይ ኪዳን ቅኝት*፣ ገጽ 510-532 ላይ ነው።

I. የመጽሐፉ ስም

ሀ. በዕብራይስጥ ርዕሱ "የምስጋና መዝሙር" ወይም "ውዳሴ" ነው (*Tehillim*፣ (ቴሂሊም) መዝሙር 145)። ይህ አስገራሚ ነው፣ ምክንያቱም አብዛኞቹ መዝሙራት ሰቆቃ ወይም ምሬት በመሆናቸው።

ለ. በሴፕቱዋጂንት (LXX) *psalmos* የሚለው ርዕስ ፍችው "መሳብ" ነው። ይህ የግሪክ ቃል በመዝሙራት ጥቅም ላይ ውሏል፣ ሉቃስ 20፡42፤ 24፡44 እና ሐዋ. 1፡20 ላይ። መዝሙራት ሁሉ በሙዚቃ መሣርያ አጃቢነት ይዘመራሉ ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ይህ የሙሉው መጽሐፍ LXX ርዕስ ሆኗል።

II. ካኖናዊነቱ (ቅዱስ ቃልነቱ)

ሀ. መዝሙር የዕብራይስጥ ካኖን ሦስተኛው ምድብ ክፍል ነው፣ "ጽሑፎች" ተብሎ የሚጠራው (Kethubhim፣ Hagiographa)። ይህ የዕብራይስጥ ካኖን ምድብ የተደራጀው፡

1. የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ
   ሀ. ኢዮብ
   ለ. መዝሙር
   ሐ. ምሳሌ
2. የክብረ-በዓል መጻሕፍት (*Megilloth*)
   ሀ. ሩት
   ለ. መክብብ
   ሐ. መኃልየ መኃልይ
   መ. ሰቆቃወ
   ሠ. አስቴር
3. ታሪካዊ መጻሕፍት
   ሀ. ዳንኤል
   ለ. ዕዝራ
   ሐ. ነህምያ
   መ. ዜና መዋዕል

ለ. መዝሙር በአኪ በተደጋጋሚ ይጠቀሳል፣ ከሌሎቹ የብኪ መጻሕፍት ይልቅ።

III. ዘውግ

ሀ. ይህ ጽሑፋዊ ዓይነት በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ የተለመደ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊዎቹ መዝሙራት የውዳሴ መልክን ከባቢሎን፣ ግብፅ፣ እና ከነዓን ይጋራሉ። ሊቃውንት የቀረበ ግንኙነትን ተመልክተዋል፡

1. በመዝሙር 104፡20-30 እና በግብፃውያን ዝማሬ *Aton* (14ኛ ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ) መካከል
2. መዝሙር 29 ከሞላ ጎደል ከዑጋሪቲክ ግጥም ለ*Ba'al* ጋር መንትያ ነው፣ ከአማልክቱ ስም በቀር።

ለ. የራስ ሻምራ ጽሑፎች ከዑጋሪት ከተማ የጥንታዊ ቅርስ ግኝቶች በከነዓናዊ ግጥምና በመዝሙራት መካካል ያለውን ተመሳሳይነት ያመለክታሉ። ግኝቱ የዘማሪውን ቅርጽና ቃላት ለመገንዘብ ረድተዋል (*መልኅቅ መጽሐፍ ቅዱስ*፣ 3 ቅጾች፣ በሚትቼል ተመልከት)።

ሐ. ጽሑፋዊ መልኩ በእስራኤል ጥንታዊ ዘውግ ነበር፡

1. የሙሴ መዝሙር፣ ዘጸ. 15፡1-17
2. የማርያም መዝሙር፣ ዘጸ. 15፡21
3. የእስራኤል መዝሙር፣ ዘኁ. 21፡17-18
4. የዲቦራ መዝሙር፣ መሳፍንት 5
5. የሐና መዝሙር፣ 1 ሳሙ. 2፡1-10
6. የመሰንቆ መዝሙር ከያሻር መጽሐፍ፣ 2 ሳሙ. 1፡17-27

መ. ሦስት የመርሕ መልኮች

1. የምስጋና መዝሙራት — በተተኳሪ የመጀመር ጠባይ ያላቸው፣ እንደ “እግዚአብሔርን አመስግኑ፣” “ለጌታ ዘምሩ፣” ወዘተ ያለ
2. የኀዘን መዝሙራት — በአቤቱታ የመጀመር ጠባይ ያላቸው፣ እንደ “ጌታ ሆይ፣” ያለ፣ ምሬትን ወይም ማሳዘንን አስከትለው
3. የጥበብ መዝሙራት — ከጥበብ ሥነ-ጽሑፍ ምድቦች ጋር ተመሳሳይ የሆኑ (ማለትም፣ እንዴት በደስታ፣ በስኬታማነት፣ በመልካም ሕይወት መኖር እንደሚቻል)

IV. ደራሲነት

ሀ. የአብዛኞቹ መዝሙራት ባህላዊ ደራሲነት የተሰጠው በርዕሶቹ ወይም በመግለጫዎቹ ላይ ነው፣ እነርሱም ከሠላሳ አራት መዝሙራት በቀር በሁሉም ላይ ይኖራሉ። እነዚህን ርዕሶች ለመመልከት ሁለት መንገዶች አሉ፡

1. እነርሱ የማሶረቲካዊ ዕብራይስጥ ጽሑፎች ክፍል ናቸው፣ እንዲሁም በሴፕቱዋጂንት ውስጥ ይገኛሉ (ምንም እንኳ ዘወትር ቢለያዩም)፣ ስለዚህ፣ ካኖናዊ ናቸው። ሆኖም፣ በሙት ባሕር ጥቅሎች ላይ የተገኙት መዝሙራት እነዚህ ርዕሶችና መግለጫዎች የሏቸውም።
2. እነርሱ ዋነኛ አልነበሩም፣ በተመስጧዊ ደራስያኑ እናም መታየት የሚኖርባቸው በጥንታዊው ባህል አኳያ ነው፣ በተመስጧዊ እውነቶች ሳይሆን። ቢያንስ ሁለቱ ከሌሎቹ ካኖናዊ ጽሑፎችጋር የማይስማሙ ይመስላሉ፡
   ሀ. የመዝሙር 34  ርዕስ አልያም 1 ሳሙ. 21፡10 (የፍልስጥኤሙ ንጉሥ ስም)
   ለ. የመዝሙር 56 ርዕስ አልያም 1 ሳሙ. 21፡10 (ዳዊት እንዴት ጌት እንደተገኘ)
   ሐ. የመዝሙር 60 መግለጫዎች የሚያሳዩት 2 ሳሙ. 8፡13 እና 1 ዜና. 18፡12ን ለማዛመድ ያለውን ችግር ያመለክታሉ፣ የተገደሉትን የጠላቶች ቁጥር በተመለከተ።
3. ሌለኛው ችግር የሚሆነው የዕብራይስጡ መስተጻምር “የ” በበርካታ መንገዶች መረዳት መቻሉ ነው፡
   ሀ. “በ የተጻፈ”
   ለ. “ለ የተጻፈ”
   ሐ. “ወደ የተጻፈ”
   መ. “የዛ ጊዜ የሆነ”
   ሠ. “በዛ ምሪት ሥር የሆነ”
4. እንደማስበው ተመስጧዊ አይመስሉኝም። በእነርሱ ላይ በዚህ ሐተታ ላይ አስተያየት አልሰጥም።

ለ. የማሶረቲካዊ ዕብራይስጥ ጽሑፍ ርዕስ የደራሲዎች መጠሪያ፡

1. ዳዊት፣ (1 ሳሙኤል 16:16-18)፣ (ኤምቲ) የ73 መዝሙራት ደራሲ፤ (LXX) የ84 መዝሙራት ደራሲ፤ (ቫልጌት) የ53 መዝሙራት ደራሲ
2. ስማቸው የማይታወቅ – 50 መዝሙራት: 1፣2፣10፣33፣43፣71፣91፣ 93-97፣104-107፣118-119፣135፣137፣146-150
3. አሳፍ የዳዊት መዘምራን አለቃ (1 ዜና. 15:16-17፤ 16:5፣ “የአሳፍ ልጆች” ተጠቅሰዋል ነህ. 7:44 ላይ) 12 መዝሙራት: 50፣ 73-83
4. የቆሬ ልጆች መዝሙር፣ የሌዋውያን ዘማርያን ቤተሰብ (1 ዜና. 9:19፤ 15:17) 11 መዝሙራት: 42-49 ከ43 በቀር፤ 84-88 ፣ ከ86 በቀር
5. ጂዱቱን፣ የሌዋውያን ዘማርያን መሪዎች፣ (1 ዜና. 16:41-42፤ 25:1-3፤ 2 ዜና. 5:12) 3 መዝሙራት: 39፤ 62፤ 77
6. ሰሎሞን፣ 2 መዝሙራት: 72፤ 127፣ “በ የተጻፈ፣” “ለ የተጻፈ፣” “ወደ የተጻፈ፣” “ለ የሆኑ፣” “በዚህ ጊዜ፣” ወይም “በዚህ አቅጣጫ”
7. ሙሴ፣ 1 ሳሙኤል: 90
8. ኢዝራሂቲ (1 ዜና. 6:33፤ 15:17)
   a. ኢታን፣ መዝሙር 89 (አንዳንዶች አብርሃም እንደሆነ ያስባሉ) 1 ዜና. 15:17፣19
   ለ. ሄማን፣ 88 (እንዲሁም የቆሬ ልጅ) 1 ነገሥ. 4:31፤ 1 ዜና. 4:31፤ 15:19

ሐ. የደራሲነት ባህል፣ ከአይሁድ ጽሑፎች፡

1. ባባ ባትራ (*Baba Bathra)* 14ለ (ታልሙድ) — “የመዝሙር መጽሐፍን የጻፈው ዳዊት ነው፣ በአስር ሽማግሌዎች ርዳታ፣ በአዳም ርዳታ፣ በቀዳሚው፣ እና መልከ ጼዴቅ እና አብርሃም እና ሙሴ እና ሄማን እና ጄዱቱን እና አሳፍ እና ሦስቱ የቆሬ ልጆች”
2. ሳህንድሪን (*Sanhedrin*) 38ለ (ታልሙድ) መዝሙር 139ኝ ለአዳም ይሰጡታል፣ እንዲሁም መዝሙር 110ን ለመልከ ጼዴቅ

መ. ሴፕቱዋጂንት መዝሙራትን ለኤርምያስ፣ ሕዝቅኤል፣ ሐጌ፣ እና ዘካርያስ ይሰጣሉ (112፤ 126፤ 127፤ 137፤ 146-149)።

V. ጊዜው

ሀ. የመዝሙር ጊዜ በበርካታ ምክንያቶች አስቸጋሪ ነው፡
1. እያንዳንዱ መዝሙር የተለየ ሁነት አለው፣ እንዲጻፉ ምክንያት የሆነ
2. በአንዳንድ ነጥቦች የአንዱ መዝሙረኛ ቃላት የእምነት ማኅበረሰቡ ሆነዋል
3. መዝሙራት የተሰባሰቡት በኤዲቶሪያል ሂደት ነው፣ ወደ አምስት መጻሕፍት

ለ. መዝሙራት ግጥሞችን አካተዋል፣ ከሁሉም የእስራኤል የሕይወት ዘመናት፡
1. የአይሁድ ወግ የሚለው፡
ሀ. አዳም መዝሙር 139ን ጻፈ
ለ. መልከ ጼዴቅ መዝሙር 110ን ጻፈ
ሐ. አብርሃም መዝሙር 89ን ጻፈ
መ. ሙሴ መዝሙር 90ን ጻፈ
2. ዘመናዊው አስተምህሮት መዝሙርን ወደ ሦስት ዋና ዋና ጊዜያት ይከፋፍላል፡
ሀ. ቅድመ-ግዞት (መጻሕፍት፣ I፣ II፣ እና IV)
ለ. ግዞት (መጽሐፍ III)
ሐ. ድኅረ-ግዞት (መጽሐፍ V)

ሐ. አብዛኞቹ መዝሙራት ለዳዊት መሰጠታቸው ግልጽ ነው፡
1. ዳዊት የሙዚቃ አቀናባሪ፣ ተጫዋች እና ዘማሪ ነበር፣ 1 ሳሙ. 16፡16-18
2. እሱም የሌዋውያንን የሙዚቃ ቡድን ወይም የቤተ መቅደስ ዘማርያንን ያነሣሣና ያደራጅ ነበር፣ 1 ቆሮ. 15:1-16:43፣ 25:1-31፤ 2 Chr. 29:25-30
3. ቀዳሚዎቹ ሁለቱ የመዝሙር መጻሕፍት ለእርሱ ተሰጥተዋል፣ መዝ. 72፡20
4. የእርሱ ዝማሬዎች በሁሉም በአምስቱ የመዝሙር መጻሕፍት ላይ ይከሰታሉ

VI. የመዝሙር መዋቅር

ሀ. አጠቃላይ የሆነ ጭብጥ ወይም ፈርጅ የለም። ያለው፡
1. አጠቃላይ መግቢያ (የጻድቅ ሰው ባሕርያት) — መዝሙር 1
2. እያንዳንዱ የአምስቱ ምድቦች መጻሕፍት የሚያበቁት በምስጋና ውዳሴ ነው፣ 41:13፤ 72:18-19፤ 89:52፤ 106:48
3. አጠቃላይ መዝጊያ (ውዳሴ) – መዝሙር 150

ለ. የአምስቱ መጻሕፍት ባሕርያት
1. መጽሐፍ 1 — መዝሙር 4-41
ሀ. ከ4ቱ በቀር ሁሉም ለዳዊት ነው የተሰጡት (1፤ 2፤ 10፤ 33)
ለ. ያህዌ ሁሉን እንደሚገዛ አምላክ መጠሪያ፣ ያህዌ — 273 ለኤሎሂም —15
ሐ. ታሪካዊ መቼቱ ሊሆን የሚችለው ዳዊት ከሳኦል ጋር ግጭት ላይ በነበረበት ወቅት ነው
2. መጽሐፍ 2 — መዝሙር 42-72 (72፡20 አርታኢን ያመለክታል)
ሀ. 42-49 ለቆሬ ልጆች (ከ43 በቀር)
ለ. ኤሎሂም ሁሉን ለሚገዛ አምላክ መጠሪያ ነው፣ ኤሎሂም - 164 ለያህዌ - 30
ሐ. ታሪካዊ መቼቱ ሊሆን የሚችለው ዳዊት ንጉሥ እንደሆነ ነው
3. መጽሐፍ 3 — መዝሙር 73-89
ሀ. መዝሙር 73-83፣ አሳፍ
ለ. መዝሙር 84-88፣ የቆሬ ልጆች (ከ86 በቀር)
ሐ. 26 መዝሙር ለዳዊት ተሰጥቷል
መ. ያህዌ እንደ አምላክ መጠሪያ 44 ጊዜ፤ ኤሎሂም 43 ጊዜ
ሠ. ታሪካዊ መቼቱ ሊሆን የሚችለው የሶርያ ቀውስ ነው
4. መጽሐፍ 4 — መዝሙር 90-106
ሀ. መዝሙር 101፤ 103 ለዳዊት
ለ. መዝሙር 90 ለሙሴ
ሐ. ቀሪዎቹ ሁሉ ስማቸው ላልታወቀ
መ. ያህዌ 104 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፤ ኤሎሂም - 7 ጊዜ
ሠ. ታሪካዊ መቼቱ ሊሆን የሚችለው የባቢሎን ቀውስ ነው
5. መጽሐፍ 5 — መዝሙር 107-150
ሀ. መዝሙር 119 የቀጠለ መስቀልያ ነው፣ በእግዚአብሔር ቃል
ለ. ያህዌ 236 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፤ ኤሎሂም 7 ጊዜ

ሐ. መዝሙር 146-150 የምዝጋና ዝማሬዎች ናቸው፣ ሁሉም "ሃሌ ሉያ (እግዚአብሔርን አመስግኑ)" በሚል የሚጀምሩ
መ. ታሪካዊ መቼቱ ሊሆን የሚችለው በእግዚአብሔር የወደፊት ባርኮት ላይ ተስፋ ማድረግ ነው

ሐ. መዝሙራትን ቁጥር መስጠት ይለያያል
1. የአይሁድ ወግ
   ሀ. Berachoth 9ለ – መዝሙር 1 እና 2 እንደ 1 ተቆጥረዋል
   ለ. Shabbath 16 — አጠቃላይ የመዝሙራት ቁጥር 147 ነበር፣ ከያዕቆብ ዕድሜ ዘመን ጋር እንዲገጥሙ
2. የአይሁድ ትርጉም
   ሀ. መዝሙር 9 እና 10 አንድ ላይ ሆነው አንድ መስቀልያ መዝሙር ይሠራሉ
   ለ. መዝሙር 114 እና 115 አንድ ላይ ሆነው፣ ሁለቱም የሃለል (Hallel) መዝሙር ይሆናሉ
   ሐ. መዝሙር 116 እና 147 እያንዳንዳቸው ለሁለት ይከፈላሉ
3. የመዝሙራት ቁጥር ሊዛመድ የሚችለው ከዓመታዊው የቅዱስ ቃሉ ንባብ ዑደት ጋር ነው ከጥንታዊው ምኩራብ

መ. መዝሙራትን ለመመደብ ናሙና መንገዶች:
1. በጭብጥ ወይም በርዕስ
   ሀ. የምስጋና ዝማሬዎች
      (1) ለእግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ፣ 8፤ 19፤ 104፤ 139፤ 148
      (2) ለእግዚአብሔር ባጠቃላይ፣ 33፤ 103፤ 113፤ 117፤ 134-136፤ 145-147
   ለ. ምስጋና የማቅረብ ዝማሬዎች፣ 9-10፤ 11፤ 16፤ 30፤ 32፤ 34፤ 92፤ 116፤ 138
   ሐ. ሰቆቃ/ሙሾ/አቤቱታ
      (1) የተጠቃለለ፣ 12፤ 14፤ 44፤ 53፤ 58፤ 60፤ 74፤ 79፤ 80፤ 83፤ 85፤ 89፤ 90፤ 94፤ 106፤ 123፤ 126፤ 137
      (2) ተናጠላዊ፣ 3-7፤ 3፤ 17፤ 22፤ 25-28፤ 31፤ 35፤ 38-43፤ 69-71፤ 86፤ 88፤ 102፤ 109፤ 120፤ 130፤ 139-143
   መ. የንግሥና ዝማሬዎች
      (1) እግዚአብሔር ንጉሥ፣ 47፤ 93፤ 96-99
      (2) የእስራኤል ንጉሥ ወይም መሲሕ፣ 2፤ 18፤ 20፤ 21፤ 45፤ 72፤ 89፤ 101፤ 110
   ሠ. የጽዮን ዝማሬ፣ 46፤ 48፤ 76፤ 84፤ 87፤ 122
   ረ. የቅዱስ ሥርዓታት ዝማሬ
      (1) የኪዳን መታደስ፣ 50፤ 81
      (2) ክህነታዊ ቡራኬ፣ 134
      (3) ስለ ቤተ መቅደስ፣ 15፤ 24፤ 68
   ሰ. የጥበብ ዝማሬዎች፣ 36፤ 37፤ 49፤ 73፤ 111፤ 112፤ 127፤ 128፤ 133
   ሸ. በያህዌ ታማኝነት ባለ እምነት ዝማሬ፣ 11፤ 16፤ 23፤ 62፤ 63፤ 91፤ 121፤ 131
   ቀ. የሐሰት አማልክትንና ጣዖት አምላኪነትን መኮነን፣ 82፤ 115
2. በደራሲው ወይም በተናጋሪው
   ሀ. የዳዊት ዝማሬ፣ በአብዛኛው ያህዌን በመጠቀም፣ እንደ መለኮት ስም፣ መዝሙር 1-41
   ለ. የዳዊት ዝማሬ ባብዛኛው ኤሎሂምን እንደ መለኮት ስም በመጠቀም፣ መዝሙር 51-72
   ሐ. የዳዊት ሌዋዊ ሙዘቀኞችና ዘማርያን ዝማሬ
      (1) ቆሬና ልጆቹ፣ መዝሙር 42-49፤ 84-88
      (2) አሳፍና ልጆቹ፣ መዝሙር 73-83
   መ. የአመስጋኞች ዝማሬ፣ መዝሙር 111-118፤ 140-150
   ሠ. የአምልኮ ተጓዦች፣ ወደ ኢየሩሳሌም በበዓል ቀን ለአምልኮ የሚመጡ ዝማሬ፣ መዝሙር 120-134
3. በታሪካዊ ሁነቶች፣ በእስራኤል ታሪክ፣ በመግለጫው ወይም በይዘቱ ላይ በመመሥረት፣ መዝሙር 14፤ 44፤ 46-48፤ 53፤ 66፤ 68፤ 74፤ 76፤ 79፤ 80፤ 83፤ 85፤ 87፤ 108፤ 122፤ 124-126፤ እና 129

ሠ. ተዛማጅ መዝሙራት
1. መዝሙር 14 እና 53 አንድ ዓይነት ናቸው፣ ከእግዚአብሔር ስም በቀር
   ሀ. መዝሙር 14 ያህዌ አለው
   ለ. መዝሙር 104 ኤሎሂም አለው
2. መዝሙር 103 እና 104 ተያይዘዋል:
   ሀ. ተመሳሳይ መክፈቻና መዝጊያ
   ለ. መዝሙር 103 ያህዌ አለው፣ እንደ አዳኝና ተቤዢ
   ሐ. መዝሙር 104 ኤሎሂም አለው፣ እንደ ፈጣሪና ሰጪ (መጋቢ)
3. መዝሙር 32 እና 51 ሁለቱም ሊያያዙ የሚችሉት ከዳዊት ኃጢአት ከቤርሳቤህ ጋር ነው
4. መዝሙር 57፡7-11 እና 60፡5-12 ከመዝሙር 108 ጋር ተደባልቀዋል

5. *መዝሙር* 18 ከ2 ሳሙ. 21፡1-51 *ተደግሟል*

ረ. 150 *መዝሙራት* በ5 *መጻሕፍት ለምን*

1. ሊሆን የሚችለው 150 *መዝሙራት* ትይዩ የሚሆኑት፣ ከ150 የምኵራብ ምድቦች፣ የሕጉ የሰንበት ቀን የአደባባይ ንባብ *ጋር* ነው
2. አምስቱ *መጻሕፍት* ትይዩ ሊሆኑ የሚችልት ከአምስቱ የሙሴ *መጻሕፍት ጋር* ነው

VII. *ሙዚቃዊ ቃላት* በዝማሬ

ሀ. *ሙዚቃዊ ቃላት* በመግለጫዎቹ የተለያዩ ዓይነት *መዝሙራትን ለመግለጽ* ጥቅም ላይ የዋሉ

1. *MIZMOR* ሚዝሞር ማለት "ከር *መግረፍ*" (የመሰንቆ ጅማት መሳብና መልቀቅ) ማለት ነው። እነዚህም *መዝሙራት* የሚዘመሩትና በሙዚቃ *መሣርያ* የሚታጀቡት ነበሩ። እነዚህም 57 ዓይነቶች ናቸው።
2. *SHIR* ሺር የሚያመለክተው ሁሉንም ዓይነት ዝማሬዎችን ነው። እነዚህም 30 ዓይነቶች ናቸው።
3. *MASCHIL* ወይም *MASKIL* የሚጠቅሱት የተለየ ጥበብ ዝማሬዎችን ወይም ትምህርታዊ ዝማሬዎችን ነው። እነዚህም 30 አሉ።
4. *MITCHTAM* ወይም *MITKHTAM* – የዚህ *ቃል* ፍቺው አልተረጋገጠም። ሊሆን ከሚችሉት
   ሀ. የዕብራይስጥ *ሥር*፣ እርሱም የሚሆነው "ወርቃማ" ወይም "የከበረ"
   ለ. ከአካድያን *ሥር*፣ እርሱም የሚሆነው "የተደበቀ" ወይም "ይፋ ያልሆነ"
   ሐ. ከዓረብኛ *ሥር*፣ እርሱም የሚሆነው "ማስተስረይ" ወይም "ይቅር ማለት ነው"
   እንዲህ ዓይነቶች 6 አሉ።
5. *PALAL* ማለት ጸሎት ነው። እሱም የዳዊትን *መዝሙር ለመግለጽ* ጥቅም ላይ የዋለ ነው፣ መጽሐፍ I እና II (*መዝሙር* 72:20)። እሱም ደግሞ በመዝሙር 17፤ 86፤ 90፤ 102፤ 142 *መግለጫዎች* ላይ ይገኛል፤ እንዲሁም 122።

ለ. *ሙዚቃዊ ቃላት* መዝሙርን ስለ መጫወት ወይም ስለመዘመር የሚገልጹ

1. *SELAH* 71 ጊዜ በ39 *መዝሙራት* እና ዕን. 3:3፣ 9፣ 13 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል። ፍችው አልተረጋገጠም። በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ:
   ሀ. ከ LXX "ጣልቃ የሚገባ" ለተመስጦ ወይም ድራማዊ ሁኔታ
   ለ. ከዕብራይስጥ *ሥር* "ከፍ ማድረግ፣" ስለዚህ፣ ማንሻ ወይም ከፍ ያለ ሙዚቃ
   ሐ. ራቢዎች የሚሉት፣ እሱ እንደ "አሜን፣" ማጽኛ ነው፣ ፍችውም "ዘላለም"
2. *SHIGGAION* ወይም *SHIGIONOTH* ጥቅም ላይ የዋለው *መዝሙር* 7 እና ዕንባቆም 3 ላይ ነው። እሱም ሰቆቃ ወይም ሙሾ ነው፣ ኀዘንን የሚገልጽ። እሱም ከፍ ያለ ቅኔአዊ መልክ አለው።
3. *NEGINOTH* ጥቅም ላይ የዋለው 6 ጊዜ ነው፣ *መዝሙር* እና ዕን. 3:19 ላይ። ፍችውም "በሚገረፉ የሙዚቃ *መሣርያዎች*" ነው።
4. *SHEMINITH* ጥቅም ላይ የዋለው ሁለት ጊዜ ነው። ፍችውም "በሙዚቃ *ቃናዎች*" ወይም "በስምንቶ" ነው። እሱም የ *ALAMOTH* ተቃራኒ ነው፣ ስለዚህ ለወንድ ድምጾች ሊሆን ይችላል (1 ዜና. 15:21)።
5. *ALAMOTH* 4 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። እሱም ቀጭን የሴት ድምጽን ያመለክታል (1 ዜና. 15:20)።
6. *MECHILOTH* አንድ ጊዜ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። ፍችውም "በትንፋሽ የሙዚቃ *መሣርያዎች*"
7. *GITTITH* 3 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል። ፍችውም "በበገና" ነው።
8. በርካታ ማጣቀሻዎች አሉ፣ ተለይተው በተሰየሙ *ቃናዎች*፣ *መዝሙር* 9፤ 22፤ 45፤ 53፤ 56፤ 57-59፤ 60፤ 62፤ 69፤ 75፤ 77፤ 80፤ and 88

VIII. *የመዝሙራት ዓላማ*

ሀ. እስራኤላውያን የሚያምኑት ሕይወት ሁሉ ከእግዚአብሔር *ጋር* በኪዳን እንደሚዛመድ ነው። *መዝሙራት* ከሰዎች ወደ እግዚአብሔር የተለቀቁ፣ ጥልቅ የሆኑ የሕይወት ስሜቶች ናቸው (አድናቆትና ቅርበት)። እነርሱም የሚሠሩት በአብሮነት አምልኮ ላይ ነው፣ እንዲሁም በግለሰባዊ መሰጠቶች። እነርሱም አምልኳዊ *መንገዶች* ናቸው የእስራኤልን *ታሪክ*ና *ሥነ-መለኮት* ለማስታወስና በንግግር *ለመግለጽ*።

ለ. እስራኤል የሚያምኑት በአንድና አንድ ብቸኛ አካል፣ ተንከባካቢ አምላክ ነው፣ እነርሱም የእርሱ ፍቅር የተለዩ ሰዎች ናቸው። እምነት ቅዱስ *ምሥጢራዊ* ወይም መርሐዊ አይደለም፣ ነገር ግን ግለሰባዊና የየዕለቱ እንጂ። የመዝሙሮቹ ቅኔአዊ መልክ ከእግዚአብሔር *ጋር* ያለንን ሃይማኖታዊነት ግለሰባዊነት *ለመግለጽ* ይረዳናል። የብኪ ዋናው *ገጸ-ባሕርይ* እግዚአብሔር ነው!

ሐ. ሁሉም መዝሙራት የሚጀምሩት ለግለሰቦች ግለሰባዊ እምነትን ለመግለጫ ነው፣ ኋላ ላይም የእምነት ማኅበረሰቡ የሚጠቀምበት (መዝሙር 23፤ 139፣ ወዘተ)።

መ. ከአኪ የመዝሙራት የጥቅስ አጠቃቀም አኳያ ግልጽ የሆነው እነርሱ መገለጦች ናቸው፣ ብሎም ስሜት-ነክ። እነርሱ ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ስብዕና፣ ስለ ኃጢአት፣ ስለ ተስፋ፣ ስለ መሲሕ፣ እና መታደስ እውነትን ያንጸባርቃሉ።

## IX. ትርጓሜያዊ ደንቦች

ሀ. ሐተታው መዝሙርን ለመተርጎም የሚሻው

1. በታሪካዊ መቼታቸው (ማለትም፣ ርዕዮተ-ዓለም)
2. በዘውጋቸው
3. የአኪ ደራስያን መዝሙርን (LXX) የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌል ለመግለጥና ለማብራራት እንዴት እንደተጠቀሙበት በመመርመር
4. በመጨረሻም፣ እነዚህን እውነቶች በየዕለቱ ሕይወታችን እንዴት እንደምንጠቀምበት፤ ነገር ግን ይህ ጠቀሜታ ቅደም ተከተሉ ቁ. 1፣2፣3 መሆን አለበት!

ለ. ትይዩዎችን መተንተን መርጫለሁ፣ ነገሮቹን በመዘርዘር። ይህም ዘውጉን የሚጥስ ነው፣ ነገር ግን ዘመናዊዎቹን ምዕራባዊ ምሑራንን እንደሚረዳቸው ተስፋ አደርጋለሁ፣ የዋናውን ደራሲ አጽንዖትና ይዘት ይመለከቱ ዘንድ።

ሐ. እያንዳንዱ አንባቢ/ተርጓሚ የዋናውን ደራሲ ዋነኛ ነጥቦች መፈለግ ይገባዋል፣ እናም የገዛ ራሱን/ራስዋን ጣልቃ ሳያስገባ። ይህ በጥንታዊ፣ ቅኔአዊ መጽሐፍ ላይ ያስቸግራል። ዘመናዊዎቹ መዝሙርን ዘወትር የሚያነቡት እንደ ጧት ጋዜጣ ነው፣ በገዛ ቋንቋቸውና ባህላቸው ለእነርሱ በቀጥታ እንደተጻፈ። በዚህ የትርጓሜ ዘዴ አንዱን መዝሙር የሆነ ነገርን ስለ አንድ ነገር እንዲል ሊያደርገው ይችላል!

ለእያንዳንዱና ለሁሉም አንጓ አንድ ዋነኛ ነጥብ ሊኖረው ይገባል። ችግሩ፣ አንጓዎች ቴክኒካዊ ጉዳይ አለመሆናቸው ነው፣ የተያያዥ ሐሳብ ጉዳይ እንጂ። እነዚህን ጥንታዊ ግጥሞች የቱጋ እንደምንመድባቸው ሁላችንም ጥረት ማድረግ ይኖርብናል፣ እንዲሁም በቂ እውነት/ነጥቦች ለመያዛችን ርግጠኞች መሆን አለብን፣ እንደ ዋነኛው ተመስጧዊ ደራሲ።

መ. አንድ የመጨረሻ ነጥብ፣ ለእኔ አኪ ትክክለኛ የብኪ ተርጓሚ ነው። መዝሙራት አዲስ ኪዳን አይደሉም ነገር ግን የሙሴ ኪዳን እንጂ! እነርሱ መተርጎምና መተግበር ያለባቸው ከአኪ መገለጥ አኳያ ነው።

# መዝሙር 1
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች*

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ጻድቅና ኃጢአተኛ ተነጻጽረዋል የኤምቲመግቢያ የሌለው | የጻድቅ መንገድና የክፉ ፍጻሜ | የጻድቅና ኃጢአተኛ ተነጻጻሪ ዕጣ-ፈንታ (የጥበብ መዝሙር) | እውነተኛ ደስታ | ሁለቱ መንገዶች |
| 1:1-3 | 1:1-3 | 1:1-3 | 1:1-3 | 1:1-2 |
| | | | | 1:3-4a |
| 1:4-6 | 1:4-6 | 1:4-6 | 1:4-6 | |
| | | | | 1:4ለ-6 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

---

*ተመስጧዊ ባይሆኑም፣ የአንቀጽ ምድቦች የሚከተለውን የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ለመረዳት ቁልፍ ናቸው። እያንዳንዱ ዘመናዊ ትርጉም አንቀጾቹን መድቦ ማጠቃለያውን እንዲያቀርብ ተደርጓል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ማዕከላዊ ርዕስ፣ እውነት ወይም አስተሳሰብ አለው። እያንዳንዱ ቅጂ ያንን ርዕስ በራሱ የተለየ መንገድ አጽዕሮቱን አስፍሯል። ጽሑፉን ስታነበው፣ የትኛው ትርጉም በርዕሰ ጉዳይም ሆነ በቁጥር ምድቦች ከአንተ መረዳት ጋር እንደሚስማማ ራስህን ጠይቅ።

በእያንዳንዱ ምዕራፍ በቅድሚያ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ ይኖርብሃል፣ እንዲሁም ርዕሰ ጉዳዮቹን መለየት (አንቀጾቹን)። ከዚያም ያንተን መረዳት ከአዲሶቹ ትርጉሞች ጋር ማወዳደር ይኖርብሃል። መጽሐፍ ቅዱስን ልንረዳ የምንችለው የዋናውን ጸሐፊ ሐሳብ ምን እንደሆነ የሱን አመክኖአዊ (ሎጂክ) እና አቀራረቡን ስንረዳ ነው። ዋነኛው ጸሐፊ ብቻ ነው ተመስጧዊው— አንባብያን መልዕክቱን ለመቀየርም ሆነ ለማሻሻል መብት የላቸውም። የመጽሐፍ ቅዱስ አንባቢዎች ተመስጧዊውን እውነት በየዕለቱና በሕይወታቸው ሁሉ ተግባራዊ ለማድረግ ኃላፊነት አለባቸው።

***ማስታወሻ፡- ሁሉም ሙያዊ ቃላትና አጽሕሮተ ቃላት በሙሉ በቅጥያ አንድ፣ ሁለት፣ እና ሦስት ላይ ተብራርተዋል።***

### ዐውደ ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ ለመዝሙር አጠቃላይ መግቢያ ነው። ካይሌ ያትስ በአስደናቂ መጽሐፉ *ከመዝሙር መስበክ* ገጽ 115-124፣ ይህ መዝሙር የሚገልጸው "የሰውን መንግሥት" ነው።
1. ባሕርዩን
2. ተጽዕኖውን
3. ጸባዩን
4. ዕጣ-ፈንታውን

ለ. ይህ መዝሙር የሚገልጸው ልማዳዊውን የአይሁድ ትምህርት ነው፣ በዚህ ሕይወት ጻድቅ እንደሚባረክና ኃጢአተኛ እንደሚቀጣ (ማለትም፣ ሁለቱ መንገዶች፣ ዘዳ. 30፡1፣15-20)። ተመሳሳይ ዓይነት ሰዎች አሉ፣ በተመሳሳይ መልኩ የሚገለጹ፣ ኤር. 17፡5-8።

ሐ. ኢየሱስ መዝሙር 1ን እንዳለ ተጠቅሞበታል፣ ለተራራው ስብከት መሠረታዊ ፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፣ ማቴዎስ 5-7 ላይ።
በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ እነዚህ ቃላት ለሰዎች ሁሉ የተባሉ አይደሉም፣ ነገር ግን ለኪዳኑ ሕዝብ እንጂ፣ የያህዌን መገለጥ ለሚያውቁት ሰዎች፣ ነገር ግን እሱን ላለመቀበል ለመረጡት። የሚመስለውም፣ ማቴ. 7፡13-14 ደግሞ የተመሠረተው በዚሁ ተመሳሳይ ዋነኛ የእምነት ገጽታ ላይ ነው። ከዚህ በታች ያለው ማስታወሻ በማቴዎስ ላይ ካለው የእኔ ሐተታ ላይ ነው። አጠቃላዩን ሐተታ www.freebiblecommentary.org. ላይ መመልከት ትችላላችሁ።

**ማቴዎስ 7**

**7፡13** ይህ ቁጥር የሚያመለክተው (1) በበሩ መግባትንና ከዚያም በመንገዱ መሄድን ነውን፤ ወይስ (2) በመንገዱ መራመድን፣ እሱም ወደ በሩ ወደሚያደርሰው፤ ወይስ (3) እሱ የዕብራይስጥ ትይዩነት ምሳሌ ነውን? በሩ በቅድሚያ የሚከሰትበት ሐቅና ከዚያም መንገዱ የሚሆንበት አንድምታው፣ ይህ የሚያመለክተው፣ አንዱ እግዚአብሔርን በግል መንገድ በኢየሱስ ትምህርት በኩል ለማወቅ ሲመጣ ነው፣ ከዚያም አዲስ የመንግሥት ሕይወትን ይኖራል። አንዳንዶቹ እነዚህ ምስክርነቶች ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ ደኅንነት ሦስትዮሽ ገጽታ ሊሰጡ ይችላሉ፡ (1) መነሻ እምነት እና ንስሐ፤ (2) ክርስቶስን-መሰል የሕይወት ስልት፤ እና (3) የፍጻሜ ዘመን ማጠቃለያ። ይህ ምሳሌ ከሉቃስ 13፡23-27 ጋር ትይዩ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "የበር አጠቃቀም" አኪ 6፡6 ላይ።

▣ "ጠባቡ ደጅ" ይህ ዓይነቱ ምሳሌያዊ እውነት ከልማድ አኳያ የሚታወቀው "ሁለት መንገዶች" በሚል ነው (ዘዳ. 30፡15፣ 19፤ መዝ. 1፤ ምሳ. 4፡10-19፤ ኢሳ. 1፡19-20 እና ኤር. 21፡8)። ኢየሱስ ለማን እንደተናገረ ለመለየት አስቸጋሪ ነው፡ (1) ለሐዋርያት፣ (2) ለፈሪሳውያን፣ ወይም (3) ለሕዝቡ። አጠቃላይ ዐውደ-ጽሑፉ አንድምታው፣ ቁጥሩ የሚዛመደው ከ5፡20 እና 5፡48 ጋር ነው። እንደዚያ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ይህ የሚያመለክተው የደጁ የክልከላ ባሕርይ ሕግጋት አይደሉም፣ እንደ ፈሪሳውያን ሕጋዊነት፣ ነገር ግን የሕይወት ስልት ፍቅር እንጂ እሱም ከክርስቶስ ጋር ካለ ግንኙነት የሚፈልቅ። ክርስቶስ ሕግጋት አሉት (ማቴ. 11፡29-30)፣ እነርሱ ግን ከተለወጠ ልብ የሚመነጩ ናቸው! ይሄንን ቁጥር ወስደን በአይሁድ-አሕዛብ ጽንሰ-ሐሳብ ግንኙነት ጋር ብናደርገው (ዝኪ. 6፡7፣32)፣ እንግዲያውስ እሱ የሚዛመደው በኢየሱስ እንደ አዳኝ (ደጅ) እና ጌታ (መንገድ) ማመን ነው።

ከቁ. 13-27 ጀምሮ ተለጣጣቂ የሆኑ ተቃርኖዎች ከሃይማኖት ሰዎች ጋር ይዘመዳሉ።

1. የሁለቱ መንገዶች ሃይማኖታዊ ተግባርን መፈጸም (ቁ. 13-14)
2. ሁለት ዓይነት ሃይማኖታዊ መሪዎች (ቁ. 15-23)
3. የሃይማኖታዊ ሕይወት ሁለቱ መሠረቶች (ቁ. 24-27)

ጥያቄው የትኞቹን ሃይማኖታዊ ሰዎች ነው ኢየሱስ የጠቀሰው የሚል አይደለም፣ ነገር ግን ሃይማኖታዊ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፍቃድ በተረዱት መጠን እንዴት ምላሽ ሰጡ ነው። አንዳንዶች ሃይማኖትን እንደ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ማግኛና መወደሻ እንዲሁም ረብ ከሰዎች ለማግኘት ይጠቀሙበታል። እሱም "እኔ" እና "አሁን" ተኮር የሕይወት ስልት ነው (ኢሳ. 29፡13፣ቆላ. 2፡16-23)። እውነተኞቹ ደቀ-መዛሙርት ሕይወታቸውን የሚመሩት ከኢየሱስ ቃላት አኳያ ነው፣ ስለ አሁኑና ስለሚመጣው የእግዚአብሔር መንግሥት።

▣ **"ወደ ጥፋት የሚወስደው ደጅ ሰፊ መንገዱም ትልቅ ነውና"** "መንገድ" ሊሆን የሚችለው (1) የሕይወት ስልት ዘይቤ እና (2) የቤተ ክርስቲያን የድሮ መጠሪያ (ሐዋ. 9፡2፤ 19፡9፣23፤ 22፡4፤ 24፡14፣22፤ 18፡25-26)። ይህ ቁጥር የሚያመለክተው ደኅንነት ቀላል ውሳኔ አለመሆኑን ነው፣ እሱም በባህል ከተያዘው ጋር የሚገጥም፣ ነገር ግን በሕይወት ላይ መሠረታዊ ለውጥ ያለው፣ ይኸውም ለእግዚአብሔር መርሖዎች ከመታዘዝ የሚመነጭ። አንደኛው መንገድ ወደ ጥፋት መውሰዱን የሚያመለክተው ሐቅ የሚያሳየው ከእግዚአብሔር የተለየ ሕይወት የሚኖሩ ሰዎችን የመጨረሻ ውጤት ነው። እነርሱ ዘወትር ሃይማኖታዊ ይመስላሉ (ኢሳ. 29፡13፤ ማቴ. 7፡21-23፤ ቆላ. 2፡23)!

ይህ ሐረግ ሁነኛ የግሪክ የጽሑፍ ልዩነቶች አሉት። በቁጥሩ መጀመሪያ ላይ የሚለው፣ "በጠበበው ደጅ ግቡ" ነው፣ ነገር ግን በሁለተኛው አጋማሽ ላይ "ደጅ" ተገድፏል፣ በትልልቁ ክብ ፊደላት የእጅ ጽሑፎች ℵ*፣ አንዳንድ የድሮ የላቲን የእጅ ጽሑፎች፣ አንዳንድ ቫልጌት የእጅ ጽሑፎች፣ Diatessaron፣ እና የግሪክ ጽሑፎች፣ በክሌመንት እና ኢዩሲበስ ጥቅም ላይ የዋሉ። እሱም የሚገኘው በክብ ፊደላት ℵ፣ B፣ C፣ L፣ W፣ እና በአንዳንድ ጥንታዊ ላቲን፣ ቫልጌት፣ ሲሪያክ፣ እና ኮፕቲክ የእጅ ጽሑፎች ላይ ነው። ስለዚህ ጥያቄው፣ "እሱ የገባው ለማመዛዘን ነው" ወይስ "በድንገት የሆነ ነው?" ዩቢኤስ[4] ረጅሙን ጽሑፍ ይሰጠናል (ማለትም፣ የእርሱን መካተት) የ "ለ" ደረጃ፣ (ከሞላ ጎደል ርግጠኛ)። ሆኖም፣ የእርሱ መካተትም ሆነ አለመካተት የጽሑፉን ፍቺ አይለውጠውም። ይህም በአብዛኛው የአኪ ልዩነቶች ላይ እውነት ነው፣ አሁን ባሉት 5300 የግሪክ አዲስ ኪዳን! ብሩስ ሜትዝገርን ተመልከት፣ *የግሪክ አዲስ ኪዳን ጽሑፋዊ ሐተታ* ገጽ 19።

**7፡14** "በቀላል-አማኞዊነት" ጊዜ ይህ አስፈላጊ ሚዛን ነው! ይህ ማለት ክርስትና በሰዎች ጥረት ላይ ጥገኛ ይሆናል ማለት አይደለም፣ ነገር ግን ይልቁን የእምነት ሕይወት በስደት የተሞላ ነው ለማለት እንጂ። "ጠባብ" በዚህ ቁጥር የሚያካፍለው ተመሳሳይ ሥርወ-ቃል ነው፣ እንደ "መከራ' ወይም "ስደት" በሌሎች የአኪ ምንባቦች ላይ። ይህ አጽንዖት የማቴ. 11፡29-30 ሁነኛ ተቃራኒ ነው። እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ባሕርያቸው እንደ "ደጅ" እና "መንገድ" ሊወሰድ ይችላል። ወደ እግዚአብሔር የመጣነው በኢየሱስ ነው፣ እንደ እግዚአብሔር ነጻ ስጦታ (ሮሜ. 3፡24፤ 5፡15-17፤ 6፡23፤ ኤፌ. 2፡8-9)፣ ነገር ግን አንድ ጊዜ ካወቅነው ትልቅ ዋጋ ያለው ዕንቁ ነው፣ እሱን ለመከተል ያለንን ሁሉ የምንሸጥለት። ደኅንነት ፍጹም ነጻ ነው፣ ነገር ግን እሱ የሆንነውንና ያለንን ነገር ሁሉ ዋጋ የምንሰጥለት ነው።

"የሚያገኙትም ጥቂቶች ናቸው" የሚለው ሐረግ ከማቴ. 7:13 እና ሉቃስ 13:23-24 ጋር መነጻጸር ይኖርበታል። ጥያቄው "ብዙዎች ከሚድኑት ይልቅ ይጠፋሉን?" የሚል ነው። ቁጥሩ የሚያስተምረው አሃዛዊ ልዩነቶችን ነውን?

*መ. ራቢዎች መዝሙር 1 እና 2ን ወደ አንድ መዝሙር ይደባልቋቸዋል። ይህም ሊረጋገጥ የሚችለው*

1. *ሐዋ. 13፡33፣ እሱም መዝሙር 2ን "የመጀመሪያው መዝሙር" ብሎ የሚጠራው።*
2. *የ"ብፁአን" አጠቃቀም፣ መዝ. 1፡1 እና 2፡12 ላይ ጽሑፋዊ ብልሃት ሊሆን ይችላል ኢንክሉሲኦ የሚባለው*
3. *በሚያስገርም መልኩ መዝሙር 1 ሆነ መዝሙር 2 የማስተዋወቂያ ሐረግ የላቸውም፣ ኤምቲ ላይ*

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 1፡1-3**

**1ምስጉን ነው በክፉዎች ምክር ያልሄደ፥**
**በኃጢአተኞችም መንገድ ያልቆመ፥**
**በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ።**
**2ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥**
**ሕጉንም በቀንና በሌሊት ያስባል።**
**3እርሱም በውኃ ፈሳሾች ዳር እንደ ተተከለች፥**
**ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥**
**ቅጠልዋም እንደማይረግፍ ዛፍ ይሆናል**
**የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል።**

**1፡1-3** የጊዜ ነገሮች በእነዚህ የመክፈቻ ቁጥሮች ላይ እየጨመረ የመጣ ይመስላል። የዕብራይስጥ ግሦች ጊዜን አይገልጹም፣ ዐውደ-ጽሑፉን ብቻ። ሊሆን የሚችለው

1. የቁ. 1 የተጠናቀቁ ግሦች የሚገልጹት ያለፈን ጊዜ ነው (ማለትም፣ ያ ሰው እንዴት እንደኖረ)
2. የቁ. 2 ያልተጠናቀቀ ግሥ የሚገልጸው የአሁን ጊዜ ነው (ማለትም፣ ግለሰቡ በየዕለቱ የሚኖርበትን መንገድ)
3. ቁጥር 3 በተጠናቀቀ ግሥ ይጀምራል በ*ዋው* (ገጽ iii ላይ የሚጀምረውን የዕብራይስጥ ሰዋሰው ጽሑፍ ተመልከት) እሱም እንደ መባረክ ያለውን መጻዒ ሁኔታ ሊገልጽ የሚችል (ማለትም፣ የሚጠበቅ ፍሬአማነት)

**1፡1** "ምስጉን" የሚለው ቃል የብዙ ነው፣ ነገር ግን ተሳቢው ነጠላ ነው፣ "ሰው።" ይህም ሊብራራ የሚችለው

1. የብዙ ቁጥሩ የዕብራይስጥ መንገድ ነው፣ ሁሉንም የእግዚአብሔር በረከቶች ለመግለጽ
2. "ሰው" ነጠላ ብዙ ነው፣ ሁሉንም ሰዎች የሚጠቅስ፣ እግዚአብሔርን የሚያውቁና የሚታዘዙ (ማለትም፣ ያዕቆብ 1፡2-23)። በዚህ ዓይነት ነው "ዛፍ" የሚለው ቃል ቁ. 3ሀ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው።

ይህ ቃል ("ምስጉን፣" ቢዲቢ 80) ፍችው "ደስተኛ፣" "የተከበረ፣" ወይም "የታደለ" ማለት ነው (ማቴ. 5፡3-12)።

ከእግዚአብሔር ተለይቶ ማንም ሰው "ደስተኛ" ሊሆን አይችልም። የተፈጠርነው በእርሱና ለእርሱ ነው (ዘፍ. 1፡26-26፤ 3፡8)። ከፈጣሪያችን ጋር ያለን ግንኙነት ጠንካራ እስካልሆነ ድረስ፣ ሁሉም አካባቢ ሥጋዊ ሕይወት እውነተኛ፣ የመጨረሻ ደስታ ሊያመጣልን አይችልም! ይህም ግንኙነት ሊታይ የሚችል ባሕርያት አሉት!

▣ *ሦስቱን ቃል የተጠናቀቁ ግሦች ተገንዘቡ፣ እነርሱም ባሕርያዊ ድርጊቶችንና ዝንባሌዎችን የሚጠቅሱ (ማለትም፣ የተረጋጋ ባሕርይ)።*

1. በክፉዎች ምክር ያልሄደ
2. በኃጢአተኞች መንገድ ያልቆመ
3. በዋዘኞችም ወንበር ያልተቀመጠ

"ምስጉን" የታመነ ተከታይ በተቃርኖ ቁ. 1 እና በድርጊታቸው ቁ. 2 ላይ ይገለጻል።

▣ **"በክፉዎች ምክር ያልሄደ"** ይህ የሚናገረው የአንዱን የሕይወት ስልት ጉድኝት ነው። ይህ የሕይወት ስልት ላይ የሆነ አጽንዖት "መሄድ... መቆም... መቀመጥ" በሚሉት ግሦች አጠቃቀም ይጠናከራል። በምንገኝበት ቡድን ተጽዕኖ ያርፍብናል፣ በተመሳሳይ አቋማችን (1 ቆሮ. 15፡33)።

"ክፉ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 957) የሚያመለክተው ንቁዎቹን ሕግ ተላላፊዎች ብቻ አይደለም (ማለትም፣ ድርጊተኞች እና ገዳፊዎች) ነገር ግን ደግሞ ከሕይወታቸው እግዚአብሔርን የሚተዉትንም እንጂ (ማለትም፣ ተግባራዊ አምላክ-የለሾች)።

▣ **"ጌታ"** ይህ የኪዳን ስም ነው፣ ለእስራኤል መለኮት፣ ያህዌ።

## ልዩ ርዕስ፡ የመለኮት ስሞች

ሀ. ኢል ቢዲቢ 42፣ ኬቢ 48)

1. ዋነኛው የዚህ ጥንታዊ ቃል ዘውጋዊ ትርጉም ለመለኮት ርግጠኝነት የለውም፣ ምንም እንኳ በርካታ ሊቃውንት ከአካድያን ሥርወቃል የመጣ ነው ብለው ቢያምኑም፣ እሱም "ጠንካራ መሆን" ወይም "ኃይለኛ መሆን" የተገኘ ነው ቢሉም (ዘፍጥረት 17፡1፤ ዘኍ. 23፡19፤ ዘዳ. 7፡21፤ መዝ. 50፡1)።
2. በከነዓናውያን አፈ ታሪክ ታላቁ አማልክት ኢል ነው (ራስ ሻምራ ጽሑፎች)
3. በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ኢል ዘወትር ከሌሎች ቃላት ጋር አይደባለቅም። እነዚህ መደባለቆች የእግዚአብሔርን ባሕርይ መግለጫ መንገድ ሆነዋል።
   - ሀ. ኤል-ኢልዮን (እግዚአብሔር ቃላቁ ልዑል፣ ቢዲቢ 42 እና 751 II)፣ ዘፍ. 14፡18-22፤ ዘዳ. 32፡8፤ ኢሳ. 14፡14
   - ለ. ኤል- ሮይ ("የሚያይ አምላክ" ወይም "ራሱን የሚገልጽ አምላክ፣" ቢዲቢ 42 እና 909)፣ ዘፍ. 16፡13
   - ሐ. ኤል -ሻዳይ ("ሁሉን ቻይ አምላክ" ወይም "ፈጽሞ የሚራራ አምላክ" ወይም "የተራራው አምላክ፣" ቢዲቢ 42 እና 994)፣ ዘፍ. 17፡1፤ 35፡11፤ 43፡14፤ 49፡25፤ ዘጸ. 6፡3
   - መ. ኤል-ኦላም (ዘላለማዊው አምላክ፣ ቢዲቢ 42 761)፣ ዘፍ. 21፡33። ይህ ቃል ከሥነ መለኮት አኳያ የሚያያዘው እግዚአብሔር ለዳዊት ከሰጠው ተስፋ ጋር ነው፣ 2ኛ ሳሙ. 7፡13፣16
   - ሠ. ኤል -ቤሪት ("የቃል ኪዳን አምላክ፣"ቢዲቢ 42 እና 136)፣ መሳ. 9፡46
4. ኤል የሚያያዘው ከ
   - ሀ. ያህዌ መዝ. 85፡8፤ ኢሳ. 42፡5
   - ለ. ኤሎሂም ዘፍ. 46፡3፤ ኢዮብ 5፡8፣ "እኔ ኤል ነኝ፣ የአባቶቻችሁ ኤሎሂም
   - ሐ. ሻዳይ ዘፍ. 49፡25
   - መ. "ቀናተኛ" ዘጸ. 34፡14፤ ዘዳ. 4፡24፤ 5፡9፤ 6፡15
   - ሠ. "መሐሪ" ዘዳ. 4፡31፤ ነህ.9፡31፤ "ታማኝ" ዘዳ. 7፡9፤ 32፡4
   - ረ. "ታላቅና የሚያስፈራ" ዘዳ. 7፡21፤ 10፡17፤ ነህ. 1፡5፤ 9፡32፤ ዳን. 9፡4
   - ሰ. "አዋቂ" 1ኛ ሳሚ. 2፡3
   - ሸ. "ጠንካራ መጠጊያዬ" 2ኛ ሳሙ. 22፡33
   - ቀ. "ተበቃዬ" 2ኛ ሳሙ. 22፡48
   - በ. "ቅዱሱ" ኢሳ. 5፡16
   - ተ. "ኃያሉ" ኢሳ. 10፡21
   - ቸ. "አዳኜ" ኢሳ. 12፡2
   - ኀ. "ታላቅና ኃይለኛ" ኤር. 32፡18
   - ነ. "ፈራጅ" ኤር. 51፡56
5. የዋናዎቹ ብሉይ ኪዳን ሁሉም የእግዚአብሔር ስሞች ድብልቅ፣ በኢያሱ 22፡22 የሚገኙት (ኤል፣ ኤሎሂም፣ ያህዌህ፣ የተደገመ)

ለ. ኢሊዮን

1. የእሱ መሠረታዊ ፍች "ልዑል፣" "ከፍ ያለ፣" ወይም "ከፍ ያለ" (ዘፍ. 40:17፤ I ነገሥ. 9:8፤ II ነገሥ. 18:17፤ ነህ፣ 3:25፤ ኤር፣ 20:2፤ 36:10፤ መዝ. 18:13)።
2. እሱም ከሌሎች በርካታ ስሞች ጋር በአቻዊ አገባብ ጥቅም ላይ ውሏል/ለእግዚአብሔር ስም።
   - ሀ. *ኤሎሂም* - መዝ. 47:1-2፤ 73:11፤ 107:11
   - ለ. *ያህዌህ* - ዘፍ. 14:22፤ II ሳሙ. 22:14
   - ሐ. *ኤል-ሻዳይ* - መዝ. 91:1፣9
   - መ. *ኤል* - ዘኍ. 24:16
   - ሠ. *ኢላህ* - ዘወትር ጥቅም ላይ የዋለው ዳንኤል 2-6 እና እዝራ 4-7፣ ከኢላር ጋር በመቀናጀት (በአራምኛ "ልዑል አምላክ") ዳን. 3:26፤ 4:2፤ 5:18፣21
3. እሱም ዘወትር እስራኤል ባልሆኑት ጥቅም ላይ ይውላል
   - ሀ. መልከጼዴቅ፣ ዘፍ. 14:18-22
   - ለ. በለዓም፣ ዘኍ. 24:16
   - ሐ. ሙሴ፣ በዘዳ. 32:8 ስለ ሕዝቦች የተናገረው።
   - መ. የሉቃስ ወንጌል በአዲስ ኪዳን፣ ለአሕዛብ የተጻፈው፣ የግሪኩን አቻ ሁፕሲስቶስን ይጠቀማል (ዝከ. 1:32፣35፣76፤ 6:35፤ 8:28፤ ሐዋ.7:48፤ 16:17) ሐ. ኤሎሂም (ብዙ)፣ ኤሎሀ (ነጠላ)፣ በቅድሚያ ጥቅም ላይ የዋለው በቅኔ ነው (ቢዲቢ 43፣ ኬቢ 52

1. ይህ ቃል ከብሉይ ኪዳን ውጭ አይገኝም።
2. ይህ ቃል የሚያመለክተው የእስራኤል አምላክ ወይም የሕዝቦችን አማልክት ነው (ዘጸ. 12፡12፤ 20፡3)። የአብርሃም ቤተሰቦች
3. ብዙ አማልክት አምላኪዎች ነበሩ (ኢያሱ 24፡2)።
4. እሱም ለሰው ፈራጆችም ይጠቀሳል ( ዘጸ. 21:6፤ መዝ. 82:6)
5. ኤሎሂም የሚለው ቃል ለሌሎች መንፈሳዊ ሕላዌዎችም ጥቅም ላይ ይውላል (መላእክት፣ አጋንንት) እንደ ዘዳ. 32:8

(LXX)፤ መዝ. 8:5፤ ኢዮብ 1:6፤ 38:7።

6. በመጽሐፍ ቅዱስ እሱ የመጀመሪያ ማዕርግ/የመለኮት ስም ነው (ዘፍ. 1:1)። እሱ እስከ ዘፍ. 2:4 ድረስ በአጠቃሎሽ አይቀርብም፣ ከዚያም ከያህዌ ጋር ይደባለቃል። እሱ በመሠረቱ (በሥነ መለኮት) ለእግዚአብሔር የሚያመለክተው እንደ ፈጣሪ፣ ደጋፊ፣ እና ሰጪ ነው፣ በዚህ ምድር ላይ ላለ ሕይወት (መዝ. 104)።

   እሱም ተመሳሳይ ነው፣ ከኢል ጋር (ዘዳ. 32:15-19)። እሱም ደግሞ ከያህዌህ ጋር ትይዩ ነው፣ እንደ መዝ. 14 (ኤሎሂም)፣ በትክክል መዝ. 53ን ይመስላል (ያህዌህ)፣ መለኮታዊ ስሞቹ ከመቀየራቸው በቀር።

7. ምንም እንኳ የብዙ ቁጥር ቢሆንና ለሌሎች አማልክት ጥቅም ላይ ቢውልም፣ ይህ ቃል ዘወትር የሚገልጸው የእስራኤልን አምላክ ነው፤ ግን ዘወትር ነጠላ ግሥ ይይዛል፣ አሀዳዊ አጠቃቀምን ለማሳየት።
8. ይህ ቃል የሚገኘው እስራኤላዊ ካልሆኑ አንደበት ነው፣ እንደ መለኮት ስም።
   ሀ. መልከጼዴቅ፣ ዘፍ. 14:18-22
   ለ. በለዓም፣ ዘኍ. 24:2
   ሐ. ሙሴ፣ ስለ ሕዝቦች በተናገረበት ጊዜ፣ ዘዳ. 32:8
9. ያልተለመደ የሚሆነው የጥቅል ስም ለአንዱ የእስራኤል አምላክ በብዙ ቁጥር መሆኑ ነው! ምንም እንኳ እርግጠኝነት ባይኖርም፣ ንድፈ ሐሳቦቹ እነዚህ ናቸው።
   ሀ. ዕብራይስጥ በርካታ የብዙ ቁጥሮች አሉት፣ ዘወትር ለአጽንዖት የሚሆን። ከዚህ ጋር በቅርብ የሚዛመደው የዕብራይስጡ ሰዋሰዋዊ ተፈጥሮ የሚጠራው፣ "የግርማዊ ብዙ ቁጥር" ሲሆን፣ የብዙ ቁጥሩ ደግሞ ጠቅም ላይ የሚውለው ጽንሰ-ሐሳቡን ለማጉላት ነው።
   ለ. ይህ ምናልባት የሚገልጸው የመላእክትን ጉባዔ ነው፣ እሱም እግዚአብሔር በሰማይ እንደሰበሰበና ትዕዛዙን እንደሰጠ ነው (1 ነገሥ. 22:19-23፤ ኢዮብ 1:6፤ መዝ. 82:1፤ 89:5፣7።
   ሐ. ይህም ሊያመለክት የሚችለው የአኪን መገለጥ ነው፣ አንድ አምላክ በሦስት አካላት። በዘፍ. 1:1 እግዚአብሔር ፈጠረ፤ ዘፍ. 1:2 መንፈሱ ሰፈፈ እናም በአዲስ ኪዳን ኢየሱስ የእግዚአብሔር አብ ወኪል ነው፣፣ በፍጥረት ላይ (ዮሐንስ 1:3፣ 10፤ ሮሜ. 11:36፤ 1 ቆሮ. 8:6፤ ቆላ. 1:15፤ ዕብ. 1:2፤ 2:10)።

መ. ያህዌህ (ቢዲቢ 217፣ ኬቢ 394)

1. ይህ ስም የሚያንጸባርቀው መለኮትን ሲሆን፣ ኪዳንን እንደሚመሠርት አምላክ ነው፤ እግዚአብሔር እንደ አዳኝ፣ ተቤዢ! ሰዎች ኪዳኑን አፈረሱ፣ እግዚአብሔር ግን ታማኝ ነው፣ ለቃሉ፣ ለተስፋው፣ ለኪዳኑ (መዝ. 103)።

   ይህ ስም መጀመሪያ የተጠቀሰው ከኤሎሂም ጋር ተደባልቆ ነው፣ በዘፍ. 2:4። በዘፍ. 1-2 ሁለት የተፈጥሮ ሐተታዎች የሉም፣ ግን ሁለት አጽንዖቶች፡ (1) እግዚአብሔር እንደ ዩኒቨርስ (ሥጋዊ) ፈጣሪ እና (2) እግዚአብሔር ልዩውን ፍጡር የሰው ልጅን ፈጥሯል። ዘፍጥረት 2:4 የሚጀምረው በተለየ መገለጥ ነው፣ እድላዊ ሥልጣንና ተግባር ስላለው የሰው ልጅ የሚያሳይ፣ እንዲሁም የኃጢአትና የዐመጸኝነት ችግር ልዩ ከሆነው ሥልጣን ጋር ስለ መያያዙ።

2. በዘፍ. 4:26 የሚለው "ሰዎችም በእግዚአብሔር ስም መጠራት ጀመሩ" (ያህዌህ)። ሆኖም፣ ዘጸ. 6:3 የሚያመለክተው የቀድሞ የኪዳኑ ሕዝቦች (አባቶችና ቤተሰቦቻቸው) እግዚአብሔርን የሚያውቁት በኤል-ሻዳይነቱ ብቻ ነው። ያህዌህ የሚለው ስም በዘጸ. 3:13-16፤ በተለይም ቁ. 14. አንድ ጊዜ ነው የተጠቀሰው። ሆኖም፣ የሙሴ ጽሑፎች ዘወትር ቃላትን የሚተረጎሙት በታወቁት የቃላት አግባቦች ነው እንጂ፣ በሥርወ ቃል አይደለም (ዘፍ. 17:5 27:36፤ 29:13-35)። የዚህን ስም ትርጓሜ በተመለከተ በርካታ ንድፈ ሐሳቦች አሉ (ከአይዲቢ የተወሰደ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 409-11)።
   ሀ. ከዓረብ ሥርወቃል፣ "ፍጹም ፍቅርን ማሳየት"
   ለ. ከዓረብ ሥርወቃል "መምታት" (ያህዌህ እንደ ማዕበላዊ አምላክ)
   ሐ. ከዩጋርቲክ (ከነዓናዊ) ሥርወቃል "ቁንጮ ላይ መሆን"
   መ. የፎንቄውያንን ጽሑፍ ተከትሎ፣ መነሻዊ ቦዝ አንቀጽ ሲሆን ፍችውም "አንዱ የሚደግፈው፣" ወይም "የሚያጸናው አንዱ" ማለት ነው።
   ሠ. ከዕብራይስጡ ቃል "አንዱ የነበረው" ወይም "አንዱ ያለው" (በትንቢት ጊዜ ደግሞ፣ "አንዱ ወደፊት የሚኖረው")
   ረ. ከዕብራይስጡ ሂፊል ከ "ወደ መኖር የሚያመጣው"
   ሰ. ከዕብራይስጡ ሥርወቃል "መኖር" (ምሳ. ዘፍ. 3:20)፣ ፍችውም "ለዘላለም የሚኖረው፣ ብቻውን ኗሪ"
   ሸ. ከዘጸ. ዐውደ ጽሑፍ 3:13-16 ያልተጠናቀቀ ቅርጽ በተጠናቀቀ አግባብ ጥቅም ላይ የዋለ፣ "እየሆንኩኝ በነበርኩበት በቀጣይም እሆናለሁ" ወይም "ፊት በነበርኩበት በቀጣይም እሆናለሁ" (ጄ. ዋሽ ዋትስ፣ *የብሉይ ኪዳን ሰዋሰው ጥናት*፣ ገጽ 67) ሙሉው የያህዌህ ስም ዘወትር የሚገለጸው በአጽህሮተ ቃል ወይም በዋነኛ ቅርጹ ነው
      (1) ያህ (ምሳ. ሃሌሉ -ያህ፣ ቢዲቢ 219፣ ዘጸ. 15:2፤ 17:16፤ መዝ. 89:9፤ 104:35)
      (2) ያሁ ("ኢአህ" የስሞች መጨረሻ፣ ምሳ. ኢሳይያስ)
      (3) ዮ ("ጆ" የስሞች መጀመሪያ፣ ምሳ. ኢያሱ ወይም ኢዩኤል)
3. በኋለኛው ይሁዲነት ይህ የኪዳን ስም በጣም ቅዱስ ስለሆነ (ቴትራግራማቶን) አይሁድ ለመናገር ይፈሩ ነበር፣ በዘጸ. 20:7፤ ዘዳ. 5:11፤ 6:13፣ ያለውን ትዕዛዝ እንዳይጥሱ በመስጋት። ስለሆነም የዕብራይስጡን ቃል ቀየሩት፣ "ባለቤት፣" "ጌታ፣" "ባል፣" "ጌታ" —አዶን ወይም አዶናይ (የኔ ጌታ)። ወደ ያህዌህ ሲመጡ በብሉይ ኪዳን ጽሑፍ ንባባቸው "ጌታ" ብለው ያነባሉ። በዚህን ምክንያት ነው ያህዌህ በእንግሊዝኛ ትርጉሞች ጌታ የሚባለው።
4. ልክ እንደ ኢል፣ ያህዌህ ከሌሎች ቃላት ጋር ይደባለቃል፣ የእስራኤልን የኪዳን አምላክ አንዳንድ ባሕርያት አጽንዖት ለመስጠት። በርካታ የተደባለቁ ቃላት ሲኖሩ፣ ጥቂቶቹ እኒህ ናቸው።
   ሀ. ያህዌህ - ዪሬህ (ያህዌህ ይሰጣል፣ ቢዲቢ 217 እና 906)፣ ዘፍ. 22:14
   ለ. ያህዌህ - ሮፌክሃ (ያህዌህ ፈዋሽህ ነው፣ ቢዲቢ 217 እና 950፣ ቦዝ አንቀጽ)፣ ዘጸ. 15:26

ሐ. ያህዌህ - ኒሲ (ያህዌህ ዓርማዬ ነው፣ ቢዲቢ 217 እና 651)፣ ዘጸ. 17፥15
መ. ያህዌህ - ሜቃዲሽኬም (ያህዌህ የሚቀድስህ ነው፣ ቢዲቢ 217 እና 872፣ ቦዝ አንቀጽ)፣ ዘጸ. 31፥13
ሠ. ያህዌህ - ሻሎም (ያህዌህ ሰላም ነው፣ ቢዲቢ 217 እና 1022)፣ መሳ. 6፡24
ረ. ያህዌህ - ሳቦዝ (ያህዌህ የሠራዊት፣ ቢዲቢ 217 878)፣ 1ኛ ሳሙ. 1፡3፤11፤ 4፡4፤ 15፡2፤ ዘወትር በነቢያት)
ሰ. ያህዌህ - ሮ' አይ (ያህዌህ እረኛዬ ነው፣ ቢዲቢ 217 እና 944፣ ቦዝ አንቀጽ)፣ መዝ. 23፥1
ሸ. ያህዌህ - ሲድቄኑ (ያህዌህ ጽድቃችን ነው፣ ቢዲቢ 217 እና 841)፣ ኤር. 23፥6
ቀ. ያህዌህ - ሻማህ (ያህዌህ እዚያ አለ፣ ቢዲቢ 217 እና 1027)፣ ሕዝ. 48፥35

◘ **"የኃጢአተኞች መንገድ"** "መንገድ" የሚለው ቃል ሥር ትርጉሙ "ፈለግ" ነው (ዝኪ. ቁ. 6 [ሁለቴ]) እና ሌላው ቃል ለሕይወት ስልት ጥቅም ላይ ውሏል። የአኪ ታማኝ ተከታዮች በመጀመሪያ እንደ "መንገዱ" ሰዎች ይገለጹ ነበር (ሐዋ. 9፡2፤ 19፡9፥23፤ 22፡4፤ 24፡14፥22)። ይህ የሚያመለክተው መጽሐፍ ቅዱሳዊ አምነት ከዶክትሪን ውል ወይም በአምልኮ ላይ ከመሳተፍ እንደሚልቅ ነው፣ ግን ደግሞ የሕይወት ስልት ታዛዥነት እና ግላዊ ግንኙነት እንጂ (ማለትም፣ "መሄድ፣" ኤፌ. 4፡1፥17፤ 5፡2፥15)።

◘ **"የዋዘኞች ወንበር"** ሁላችንም ስለ ሕይወት ቅድመ-ግምቶች አሉን። "ዋዘኞች" (ቢዲቢ 539፣ ኬቢ 529፣ *ቃሉ* ቦዝ አንቀጽ) የሚወክለው ሃይማኖት-የለሽ ተስፋ-ቆራጭ ምስልን ነው (ማለትም፣ ኢሳ. 5፡19፤ ኤር. 17፡15፤ ሕዝ. 12፡22፥27፤ ሚል. 2፡17፤ 1 ጢሞ. 4፡1፤ 2 ጢሞ. 3፡1-5፤ 2 ጴጥ. 3፡3-4፤ ይሁዳ ቁ. 18)።

**1፡2 "ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለዋል፥"** "ሕግ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 435) ፍችው "ማስተማር" ነው። መዝሙር ላይ "ሕጉ" ዘወትር የሚጠቅሰው የእግዚአብሔርን አጠቃላይ ትምህርት ነው (መዝሙር 119)፣ የሙሴን ጽሑፎች ሳይሆን። ሕጉ ለብኪ አማኝ ሸክም አልነበረም (መዝ. 19፡7-13)፣ ነገር ግን የያህዌ መገለጥ ረዘም ላለ ንብረት፣ ሰላም፣ ደኅንነት፣ ደስታ፣ እና መትረፍረፍ፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር ራዕይ መግለጫ ቃላት (ዘዳግምንና መዝሙርን በመጠቀም)

I. *ሥርዓት፣*" ቢዲቢ 349፣ "ሕጋዊ ሰነድ፣ ደንብ፣ ወይም ሥነ ሥርዓት"

ሀ. ተባዕታይ፣ חק- ዘዳ. 4፡1፥5፥6፥8፥14፥40፥45፤ 5፡1፤ 6፡1፥24፥25፤ 7፡11፤ 11፡32፤ 16፡12፤ 17፡19፤ 26፡17፤ 27፡10፤ መዝ. 2፡7፤ 50፡16፤ 81፡4፤ 99፡7፤ 105፡10፥45፤ 148፡6

ለ. አንስታይ፣חקה- ዘዳ. 6፡2፤ 8፡11፤ 10፡13፤ 11፡1፤ 28፡15፥45፤ 30፡10፥16፤ መዝ. 89፡31፤ 119፡5፥8፥ 12፥ 6፥23፥26፥33፥48፥54፥64፥68፥71፥ 80፥ 83፥112፥124፥ 135፥ 145፥ 155፥ 171

II. "ሕግ" ቢዲቢ 435፣ "መመሪያ"

ዘዳ. 1፡5፤ 4፡44፤ 17፡11፥18፥19፤ 27፡3፥8፥26፤ 28፡58፥61፤ 29፡21፥29፤ 30፡10፤31፡9፤ መዝ. 1፡2፤ 19፡7፤ 78፡10፤ 94፡12፤ 105፡45፤ 119፡1፥18፥ 29፥34፥44፥51፥53፥ 55፥61፥ 70፥ 72፥77፥85፥92፥97፥109፥ 113፥126፥ 136፥142፥ 150፥153፥ 163፥165፥174

III. "ምስክርነቶች" ቢዲቢ 730፣ "መለኮታዊ ሕጎች"

ሀ. የብዙ፣ עדה- ዘዳ. 4፡45፤ 6፡17፥20፤ መዝ. 25፡10፤ 78፡56፤ 93፡5፤ 99፡7፤ 119፡22፥24፥46፥59፥ 79፥ 95፥ 119፥ 125፥ 138፥146፥152፥ 167፥168

ለ. ות ወይም עדת- መዝ. 19፡7፥ 78፡5፥ 81፡5፥ 119፡2፥14፥31፥36፥88፥99፥111፥129፥144፥157

IV. "መርሖች" ቢዲቢ 824፣ "ተጠያቂነት"

- መዝ. 19፡8፥ 103፡18፥ 111፡7፥ 119፡4፥15፥27፥40፥45፥56፥63፥ 69፥78፥87፥ 93፥94፥100፥ 104፥ 110፥128፥134፥141፥ 159፥168፥173

V. "ትዕዛዛት" ቢዲቢ 846

- ዘዳ. 4፡2፥40፤ 5፡29፤ 6፡1፥2፥17፥25፤ 8፡1፥2፥11፤ 10፡13፤ 11፡13፤ 15፡5፤ 26፡13፥17፤ 30፡11፥16፤ መዝ. 19፡8፤ 119፡6፥10፥ 19፥21፥32፥ 35፥47፥ 48፥60፥ 66፥ 73፥86፥96፥98፥ 115፥ 127፥131፥143፥ 151፥166፥176
- "ፍርዶች/ደንቦች" ቢዲቢ 1048፣ "ድንጋጌዎች" ወይም "ፍትሕ" ዘዳ. 1፡17፥ 4፡1፥ 5፥ 8፥ 14፥ 45፤ 7፡12፤ 16፡18፤

30፡16፤ 33፡10፥21፤ መዝ. 10፡5፤ 18፡22፤ 19፡9፤ 48፡11፤ 89፡30፤
97፡8፤ 105፡5፥7፤ 119፡7፥13፥20፥ 30፥39፥43፥52፥62፥ 75፥84፥102፥106፥120፥137፥149፥ 156፥160፥164፤ 147፡19፤ 149፡9

VI. "መንገዱን" ቢዲቢ 202፣ የያህዌ መመሪያ ለሕዝቡ የሕይወት ስልት

- ዘዳ. 8፡6፤ 10፡12፤ 11፡22፥28፤ 19፡9፤ 26፡17፤ 28፡9፤ 30፡16፤ 32፡4፤ መዝ. 119፡3፥ 5፥37፥59

VII. "ቃሉን"

ሀ. ቢዲቢ 202 - ዘዳ. 4፡10፥12፥36፤ 9፡10፥ 10፡4፥ መዝ. 119፡9፥16፥17፥25፥28፥42፥43፥49፥ 57፥65፥74፥ 81፥ 89፥101፥105፥107፥114፥130፥ 139፥147፥160፥161፥169

ለ. ቢዲቢ 57

1. “ቃል” - ዘዳ. 17:19፤ 18:19፤ 33:9፤ መዝ. 119:11፣67፣103፣162፣170፣172
2. “ተስፋ” - መዝ. 119:38፣41፣50፣58፣76፣82፣116፣133፣140፣148፣154

“ትዕዛዝ” - መዝ. 119፡158

▣ **“በቀንና በሌሊት ያስባል”** ይህ *ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 211፣ ኬ.ቢ. 237፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) የሚጠቅሰው “የለሆሳስ ንባብን” ነው፣ ያህዌ የገለጠውን እውነት። የጥንቶቹ በጸጥታ አያነቡም ነበር፣ ስለዚህ የጸጥታ ንባብ ይመረጣል።

ይህ *ግሥ* እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ አስተውል

1. የያህዌን ትምህርት ማሰብ – መዝ. 1:2፤ ኢ.ያ. 1:8
2. ራሱን ያህዌን ማሰብ – መዝ. 63:7
3. የያህዌን *ሥራዎች* ማሰብ – መዝ. 77:13፤ 143:5
4. የሚያስፈራውን ማሰብ – ኢ.ሳ. 33:18

ስለ ምንድነው የምታስቡት?

የሐሳብ ሕይወታችን የድርጊታችን የዘር መደብ ነው (ምሳ. 23፡7)። ይህ ቁጥር አጽንዖት የሚሰጠው ቀጣይነት ያለውን መርሕ ነው (ማለትም፣ ቀንና ሌሊት) በሕሊናችን የእግዚአብሔርን ፍቃድ መጠበቅ። ይህም ዋነኛው ዓላማ ነው፣ ዘዳ. 6፡8-9 ላይ ተምሳሌታዊ የተደረገው። በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ከተሰጡት አስተያየቶች እዚህጋ አክያለሁ።

**ዘዳግም 6**

**6፡8 “በእጅህም ምልክት አድርገህ እሰረው፣ በዓይኖችህም መካከል እንደ ክታብ ይሁንልህ”** በዋነኛነት ይህ ሐረግ የሚመስለው እንደ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለ ነው (LXX)። *ዐ*ውደ ጽሑፉ የሕይወት ስልት የመማር ዕድል ነው፣ የእግዚአብሔርን ቃል። ሆኖም፣ ራቢዎች ይሄንን ቃል እጅግ በጥሬው ወስደው፣ የቆዳ ክታብ በግራ እጃቸው ዙሪያ ማሰር ጀምረዋል፣ በአነስተኛ መያዣ (*tefillin*) በላዩም ከቶራ የተመረጠ ቃል የያዘ። ተመሳሳይ የሆነ ክታብም በግንባራቸው ላይ ያስራሉ። እነዚህ “የእጅ ክታቦች” ወይም “የራስ ክታቦች” (ቢ.ዲ.ቢ. 377) ደግሞ ዘዳ. 11:18 እና ማቴ. 23:5 ላይ ተጠቅሰዋል።

**6፡9 “በቤትህም መቃኖች በደጃፍህም በሮች ላይ ጻፈው”** ይህም ደግሞ ተምሳሌታዊ ምልክት ነው፣ እግዚአብሔር በቤት ሕይወታችን ብቻ ሳይሆን በማኅበራዊ ሕይወታችንም ስፍራ እንዳለው የሚያመለክት (ማለትም፣ደጅ፣ ዝኪ. 21:19፤ 22:15፣24)። እንደ በር መተላለፊያ (ቢ.ዲ.ቢ. 265) የቤት፣ ዘወትር ይታያል እንደ አጋንንት ስፍራ፣ በግሪክና በሮሜ ዓለማት፣ በአይሁድ ዓለም እሱ የሚወክለው የእግዚአብሔርን መገኘት ነው (ማለትም፣ የፋሲካ ደም የተደረገበት ስፍራ፣ ዘጸ. 12:7፣22፣23)።

“ደጆቻችሁ” (ቢ.ዲ.ቢ. 1044) የሚያመለክተው የማኅበራዊ መሰብሰቢያና የፍትሕ ስፍራ ነው (ማለትም፣ እንደ ከተማ ደጅ)። እነዚህ አነስተኛ ክታቦች እና የበር ምልክቶች ዘወትር (*mezuza*) በርካታ የተደራጁ የቅዱስ ቃሉ ምንባቦችን ይይዛሉ: ዘዳ. 6:4-9፤ 11:13-21 እና ዘጸ. 13:1-10፣11-16።

**1፡3 “እንደ ዛፍ”** ይህን በተመለከተ አስደናቂ ዘይቤ አለ፣ ኤር. 17፡5-8 ላይ። ለበረሀ ማኅበረሰብ፣ ፍሬአማ ዛፍ የጥንካሬና የብልጽግና ተምሳሌት ነው።

▣ *ግሡ* (ቢ.ዲ.ቢ. 1060፣ ኬ.ቢ. 1670፣ በጽኑ የተተከለ፣” *ቃል ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ*) ፍችውም “የተተከለ” (መዝ. 92:14፤ ኤር. 17:8፤ ሕዝ. 17:10፣22፤ 19:10፣13፤ ሆሴ. 9:13)። ይህ የሚያመለክተው ይህ ሰው፣ እንደ ሌሎቹ ሰዎች ከመነሻው ፍሬአማ አማኝ አልነበረም። ብስለት ጊዜ፣ ጥረት፣ እና በተለይም የእግዚአብሔርን ጸጋ ይወስዳል። ጳውሎስ የብኪ ጽሑፎችን ንግግር ይጠቀማል፣ ከውድቀት በኋላ የሆነውን የሰዎችን መነሻ ክፉነት ለማሳየት (ሮሜ 3፡10-18)።

1. ቁ. 10-12 – መዝ. 14:1-3፤ 53:1-4
2. ቁ. 13 – መዝ. 5:9፤ 140:3
3. ቁ. 14 – መዝ. 10:7
4. ቁ. 15-17 –ኢ.ሳ. 59:7-8
5. ቁ. 18 –መዝ. 36:1

ሁላችንም “የተተከልን” ነን፣ ከዓመጻ ወደ ባርኮት!

▣ **“የውኃ ፈሳሾች”** ይህ የብዙ ቁጥር ነው፣ የሚናገረውም የተስፋፋ የመስኖ መስመርን ነው።

▣ **“ፍሬዋን በየጊዜዋ እንደምትሰጥ፥”** ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘይቤ ነው፣ የበሰለ መንፈሳዊ ሕይወትን ለመግለጽ (ማቴ. 7፡15-27)። የእምነት ግብ ታማኝነት ነው! ይኸው ተመሳሳይ ምስላዊ የፍጻሜ ዘመን መቼት አለው፣ ራዕይ 22 ላይ።

▣ **“ቅጠልዋም እንደማይረግፍ”** ይህ የፍጻሜ ዘመን ጭብጥ ነው (ሕዝ. 47:12፤ ራዕ. 22:2)። የግብርና ዘይቤዎች እጅግ ኃይለኞች ነበሩ፣ ለገበሬዎችና ለከብት አርቢዎች፣ በከፊል ሞቃታማ አካባቢዎች።

**1፡3-4 “የሚሠራውም ሁሉ ይከናወንለታል… ክፉዎች እንዲህ አይደሉም”** ይህ የብኪ አተያይ ነው፣ ማለትም ጊዜያዊው ባርኮቶችና ርግማኖች የሚመሠረቱት በአንዱ መንፈሳዊ ሕይወት እንደሆነ (ዘዳግም 28 እና 30)።

ሆኖም፣ ይህ መመዛዘን ይኖርበታል፣ ከኢዮብ ሕይወት ጋር፣ መዝሙር 37 እና 73፣ እና ደግሞ የአኪ መገለጥ። ብኪ በኪዳን ላይ የተመሠረተ አፈጻጸም ነው ነገር ግን አኪ በጸጋ ላይ የተመሠረተ ኪዳን ነው (ኤር. 31:31-34፤ ሕዝ. 36:22-38፤ ኤፌ. 2:8-10)። ሁለቱም የሚሆኑት መልካም ተከታዮችን ለማፍራት ነው፣ እነርሱም የያህዌን ባሕርይ የሚያመለክቱ።

**መዝሙር ፡ 1፡4-6**

**[4]ክፉዎች እንዲህ አይደሉም፥**
**ነገር ግን ነፋስ ጠርጎ እንደሚወስደው ትቢያ ናቸው።**
**[5]ስለዚህ ክፉዎች በፍርድ፥**
**ኃጢአተኞችም በጻድቃን ማኅበር አይቆሙም።**
**[6]እግዚአብሔር የጻድቃንን መንገድ ያውቃልና፥**
**የክፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች።**

**1፡4 "እንደ ትቢያ"** ይህ የተለመደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘይቤ ነው፣ ለአጭር ጊዜ፣ ለጊዜአዊ፣ ወይም ወዲያው ለሚያልፍ (ዝኪ. 35:5፤ 83:13፤ ኢዮብ 21:18፤ ኢሳ. 17:13፤ 29:5፤ 40:24፤ 41:15-16፤ ኤር. 13:24፤ ሆሴ. 13:3)።

የክፉውን ፍርድ ለመመልከት ሁለት መንገዶች አሉ።

1. ጊዜያዊ — ደስታ የለሽ፣ ብልጽግና የሌለው፣ ያለጊዜ ሞት (ማቴዎስ 7)
2. የፍጻሜ ዘመን — የፍጻሜ ዘመን ፍርድ ትዕይንት፣ የአንዱ ዘላለማዊ መዳረሻ በሚገለጥበት ስፍራ (ማቴዎስ 25፤ ራዕይ 20)

**1፡5 "መቆም"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 763፣ ኬቢ 840) የሕጋዊ መቼት ትርጉም አለው (ምሳ. 19:21፤ ኢሳ. 14:24፤ ሮሜ. 8:31-38 አስታውስ)። ኃጢአተኞች/በደለኞች

1. ጉዳያቸውን ለማቅረብ መብት አይኖራቸውም
2. በፍርድ ችሎት ለመገኘት መብት አይኖራቸውም
3. ምንም ታሳቢ ማስተባበያ አይኖራቸውም
4. ለአዎንታዊ ፍርድ ምንም ተስፋ አይኖራቸውም

▣ **"ፍርድ"** ይህ የሚያመለክተው ግለሰቦች ለድርጊታቸው ተጠያቂ እንደሚሆኑ ነው፣ እናም አንድ ቀን ለእግዚአብሔር ምላሽ ይሰጡበታል (ማቴ. 25:31-46፤ 1 ቆሮ. 3:10-15፤ ራዕ. 20:11-15)። በብኪ ይህ እውነት ቀስ በቀስ ዳብሯል (ኢዮብ 19:25-27፤ ዳን. 12:2)።

▣ **"ክፉዎች... ኃጢአተኞች"** በርካታ ገላጭ መጠሪያዎች "ለማይራመዱ/ለማይቆሙ/ለማይቀመጡ" ተሰጥቷል።

1. ክፉዎች፣ ቁ. 1፣5፣6 (ቢዲቢ 957)
2. ኃጢአተኞች፣ ቁ. 1፣ 5 (ቢዲቢ 308)
3. ዋዘኞች ቁ. 1 (ቢዲቢ 539)

ኒዶቲ፣ ቅጽ. 3፣ ገጽ. 1202፣ ያህዌን የማያውቁትንና የማይከተሉትን የሚገልጹ የተለያዩ የዕብራይስጥ ቃላትን ይዘረዝራል (ማለትም፣ ጻድቅ)።

1. ክፉ ሠሪዎች – መዝ. 28:3፤ 92:7፤ 101:8፤ 141:9
2. ክፉ አድራጊዎች – መዝ. 26:5፤ 37:9፤ ምሳ. 24:19
3. ክፉ ሰዎች – መዝ. 10:15፤ ምሳ. 4:14፤ 14:19፤ 24:20
4. ጨካኝ ሰዎች – ኢዮብ 15:20፤ 27:13፤ ኢሳ. 13:11
5. ኃጢአተኞች – መዝ. 1:1፣5፤ 104:35
6. አላጋጮች –መዝ. 1:1፤ ምሳ. 9:7
7. ውሸተኞች – መዝ. 58:3
8. ተላላፊዎች – ምሳ. 2:22፤ 21:18፤ ኤር. 12:1፤ ዕን. 1:13
9. ጠላት – ኢዮብ 27:7፤ መዝ. 3:7፤ 17:9፤ 55:3

▣ **"በጻድቃን ማኅበር"** በዚህ ሐረግ እና "በፍርድ" መካከል ያለውን ትይዩነት ተገንዘቡ። እነዚህ ሐረጎች መጥቀስ ያለባቸው የእውነተኞች፣ የታማኞች ተከታዮችን መሰባሰብ ነው፣ ክፉዎች እውቅና በማያገኙበት ወይም መናገር በማይችሉበት ጊዜ።

"ማኅበር" ሊያመለክት የሚችለው

1. የአንድነት አምልኮ (ማለትም፣ መዝ. 22:25፤ 35:18፤ 40:9-10)
2. ለእግዚአብሔር ሕዝብ መጠሪያ (ማለትም፣ ዘጸ. 12:3፣6፣19፣47፤ 16:1፣2፣9፣10፣22)

## ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ

"ጽድቅ" የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪ የግድ ተከታታይ የሆነ የግል ጥናት በጽንሰ ሐሳቡ ላይ ማድረግ ያለበት ወሳኝ ርዕስ ነው።

በብሉይ ኪዳን የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚገለጸው "ትክክለኛ" ወይም "ጻድቅ" በሚል ነው። ሜሶፖታሚያዊው ቃል ራሱ የመጣው ከወንዝ ዳር ሸንበቆ ሲሆን፣ የግድግዳና የአጥርን አግድሞሽ ቀጥተኛነት መለኪያ የሚሆን የግንባታ መሣርያ ነው። እግዚአብሔር ቃሉን በዘይቤነት ለራሱ ባሕርይ መጠሪያ እንዲሆን መርጦታል። እሱ ቀጥተኛ የሆነ (የማስመሪያ) ጫፍ ነው፣ በእሱም ሁሉም ነገር የሚመዘንበት። ይህ ጽንሰ ሐሳብ የእግዚአብሔርን ጽድቅ ይገልጻል፣ እንዲሁም ለመፍረድም ሥልጣን እንዳለው።

ሰው የተፈጠረው በእግዚአብሔር አምሳል ነው (ዘፍ. 1፡26-27፤ 5፡1፣3፤ 9፡6)። የሰው ልጅ የተፈጠረው ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረው ነው። ሁሉም ፍጥረታት የተዘጋጀውና ያለው ለእግዚአብሔር እና ለሰው ልጆች መስተጋብር ተብሎ ነው። እግዚአብሔር ልዕለ ፍጡሩን ይፈልገዋል፣ የሰው ልጅ፣ እንዲያውቀው፣ እንዲወደው፣ እንዲያገለግለው፣ እንዲሁም እሱን እንዲመስል! የሰው ልጅ ታማኝነት ተፈትኗል (ዘፍ. 3)፣ እናም ሁለቱ ዋነኛ ጥንዶች ፈተናውን ወድቀዋል። ይህም በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለውን ግንኙነት አበላሽቶታል (ዘፍ. 3፤ ሮሜ 5፡12-21)።

እግዚአብሔር ኅብረቱን ለማደስና ለመመለስ ቃል ገብቷል (ዘፍ. 3፡15)። ይህንንም ያደረገው በራሱ ፍቃድና በራሱ ልጅ ነው። ሰዎች የተጣሰውን ሊመልሱት አልቻሉም (ሮሜ 1፡18-3፡20)።

ከውድቀት በኋላ፣ የእግዚአብሔር የመጀመሪያ ርምጃ፣ ለተሐድሶው የኪዳናዊ ጽንሰ-ሐሳብ የተመሠረተው በእሱ ግብዣና በሰው ልጅ የንስሐ፣ የእምነት፣ የመታዘዝ ምላሽ ነው። በውድቀት ምክንያት፣ ሰዎች ተገቢ ድርጊት ለመፈጸም አልቻሉም (ሮሜ 3፡21-31፤ ገላትያ 3)። እግዚአብሔር ራሱ መነሻውን ወስዷል፣ ኪዳን አፍራሽ የሆኑትን የሰው ልጆች ለመመለስ። ይሄንንም ያደረገው

1. ኃጢአተኛውን ሰው በክርስቶስ ሥራ በኩል ጻድቅ አድርጎ <u>ማወጅ</u> (የፍርድ ጽድቅና)
2. <u>በነጻ የተሰጠ</u> የሰው ልጅ ጽድቅ በክርስቶስ ሥራ በኩል (የተሰጠ ጽድቅ)
3. <u>የተሰጠ </u>የሚያድረው መንፈስ ጽድቅን ይፈጥራል (ሥነ ምግባራዊ ጽድቅ) በሰው ልጆች።
4. <u>መመለስ </u>የኤደን ገነት ኅብረት በክርስቶስ የእግዚአብሔርን አምሳል መለሰ (ዘፍ. 1፡26-27) በአማኞች (ግንኙነታዊ ጽድቅ)።

ሆኖም፣ እግዚአብሔር ኪዳናዊ ምላሽ ይፈልጋል። እግዚአብሔር አውጇል (በነጻ ሰጥቷል) እናም ይሰጣል፣ የሰው ልጆች ግን <u>የግድ</u> ምላሽ መስጠት አለባቸው እንዲሁም በምላሻቸው መቀጠል

1. ንስሐ
2. እምነት
3. በሕይወት ኑሮ መታዘዝ
4. መጽናት

ጽድቅ፣ ስለዚህ ኪዳናዊ ነው፣ በእግዚአብሔርና በልዕለ ፍጡሩ መካከል ያለ ሁለትዮሽ ድርጊት። እሱም የተመሠረተው በእግዚአብሔር ባሕርይ፣ በክርስቶስ ሥራ፣ በመንፈስ አስቻይነት፣ ይህም እያንዳንዱ ሰው በግሉ እና በቀጣይነት በተገቢው ምላሽ መስጠት ያለበት ነው። ጽንሰ ሐሳቡም "በእምነት መጽደቅ" ይባላል። ጽንሰ ሐሳቡ በወንጌላት ተገልጿል፣ ነገር ግን በእነዚህ ቃልት አይደለም። እሱም በመጀመሪያ የተገለጠው በጳውሎስ ሲሆን እሱም የግሪኩን ቃል "ጽድቅ" ን በተለያየ መልኩ ከ100 ጊዜ በላይ ተጠቅሟል።

ጳውሎስ የሠለጠነ ራቢ እንደ መሆኑ መጠን፣ ዲካዮሱኔ (dikaiosunē) የሚለውን ቃል በዕብራይስጥ አገባቡ SDQ በሴፕቱዋጂንት ጥቅም ላይ የዋለውን፣ ከግሪክ ሥነ ጽሑፍ ሳይሆን። በግሪክ ጽሑፎች ቃሉ የሚያያዘው፣ ለአንዱ የመለኮት ተስፋ በኅብረተሰቡ ዘንድ ለማረጋገጥ ነው። በዕብራይስጥ አግባቡ ዘወትር የሚያያዘው ከኪዳናዊ ቃላት ጋር ነው። ያህዌ ፍትሐዊ፣ ሥነምግባራዊ፣ ግብረገባዊ አምላክ ነው። እሱም ሕዝቦቹ የሱን ባሕርይ እንዲያንጸባርቁ ይሻል። የተቤዠ የሰው ልጅ አዲስ ፍጥረት ሆኗል። ይህ አዲስነት ውጤቱ አዲስ የመልካምነት የሕይወት ስልት ያሳያል (የሮማን ካቶሊክ የጽድቅ ትኩረት)። እስራኤል ቲዎክራሲያዊ (የአምላክ መንግሥት) እንደመሆኑ መጠን በሥጋዊ (የኅብረተሰቡ ደንቦች) እና በተቀደሰው (የእግዚአብሔር ፍቃድ) መካከል እንዲሁም "በጽድቅ" (ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ) ግልጽ የሆነ መለያ የለውም። ይህ ልዩነት የሚገለጠው በዕብራይስጥና በግሪክ ቃላት ነው፣ እነርሱም ወደ እንግሊዝኛ ሲተረጎሙ "ፍትሕ" (ከኅብረተሰቡ ጋር በተያያዘ) እንዲሁም "ጽድቅ" (ከሃይማኖት ጋር በተያያዘ)።

ወንጌል (መልካም የምስራች) የኢየሱስ፣ የወደቀው የሰው ልጅ ወደ እግዚአብሔር ኅብረት መመለሱን ነው። የጳውሎስ አያዎ (ፓራዶክስ) የሚሆነው፣ እግዚአብሔር በክርስቶስ በኩል በደልን ማስወገዱ ነው። ይህም ሊገኝ የሚችለው በእግዚአብሔር ፍቅር፣ ምሕረት፣ እና ጸጋ ሲሆን፣ የልጁ ሕይወት፣ ሞት፣ እና ትንሣኤ፤ እንዲሁም የመንፈስ መቃትትና ወደ ወንጌል መሳብ ነው። ጽድቅ የእግዚአብሔር ነጻ ድርጊት ነው፣ ነገር ግን መልካምነትን ሊያመነጭ ይገባል (የአውግስጢኖስ አቋም፣ እሱም የሚያሳየው ሁለቱንም፣ የተሐድሶ አጽንኦት በነጻ ወንጌል ላይ እና የሮማን ካቶሊክ አጽንኦት በተለወጠ ሕይወት በፍቅርና በታማኝነት ላይ ነው)። ለባለ ተሐድሶዎች ቃሉ "የእግዚአብሔር ጽድቅ" ተጨባጭ ባለ ሙብትነትን ሲያሳይ (ማለትም፣ ኃጢአተኛውን የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ተቀባይነት እንዲያገኝ የማድረግ ሥራ [አቋማዊ ቅድስና])፣ ለካቶሊክ ደግሞ የተሳቢ ባለሙብትነት ነው፣ ይህም እግዚአብሔርን የመምሰል ሂደት ነው፣ (ተሞክሯዊ ተራማጅ ቅድስና ነው)። በተጨባጭ ግን ሁለቱም ነው!!

በእኔ አስተያየት መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉ ከዘፍ. 4-ራዕይ 20 የተመዘገበው እግዚአብሔር የኤደንን ኅብረት እንደሚመልስ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ ኅብረት በምድራዊ መቼት ይጀምራል፣ (ዘፍ. 1-2) እናም መጽሐፍ ቅዱስ በተመሳሳይ መቼት ነው የሚያበቃው (ራዕ. 21-22)። የእግዚአብሔር አምሳልና ዓላማ ይመለሳል!

የላይኛውን ማብራሪያ ለማጠቃለል የሚከተሉትን የተመረጡ የአዲስ ኪዳን ምንባቦችን የግሪኩ ቃለት ምድብ የሚያመላክቱትን እይ።

1. እግዚአብሔር ጻድቅ ነው (ዘወትር የሚያያዘው እግዚአብሔር እንደ ፈራጅ ነው)
    - ሀ. ሮሜ 3፡26
    - ለ. 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡5-6
    - ሐ. 2ኛ ጢሞቲዎስ 4፡8
    - መ. ራዕይ 16፡5
2. ኢየሱስ ጻድቅ ነው
    - ሀ. ሐዋርያት ሥራ 3፡14፤ 7፡52፤ 22፡14 (የመሲሕ ማዕርግ)
    - ለ. ማቴዎስ 27፡19
    - ሐ. 1ኛ ዮሐንስ 2፡1፣29፤ 3፡7

3. የእግዚአብሔር ሐሳብ ለፍጥረቱ ጽድቅ ነው
ሀ. ሌዋውያን 19፡2
ለ. ማቲዎስ 5፡48 (ዝከ 5፡17-20)
4. የእግዚአብሔር ጽድቅን የመስጠትና የመፍጠር አግባብ
ሀ. ሮሜ 3፡21-31
ለ. ሮሜ 4
ሐ. ሮሜ 5፡6-11
መ. ገላትያ 3፡6-14
ሠ. በእግዚአብሔር የተሰጠ
1. ሮሜ 3፡24፤6፡23
2. 1ኛ ቆሮንቶስ 1፡30
3. ኤፌሶን 2፡8-9
ረ. በእምነት የሚቀበሉት
1) ሮሜ 1፡17፤3፡22፣26፤ 4፡3፣5፣13፤ 9፡30፤ 10፡4፣6፣10
2) 1ኛ ቆሮንቶስ 5፡21
ሰ. በልጁ ሥራ በኩል
1. ሮሜ 5፡21-31
2. 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14
3. ፊሊፐስዩስ 2፡6-11
5. የእግዚአብሔር ፍቃድ ተከታዮቹ ጻድቅ እንዲሆኑ ነው
ሀ. ማቴዎስ 5፡3-48፤ 7፡24-27
ለ. ሮሜ 2፡13፤ 5፡1-5፤ 6፡1-23
ሐ. 2ኛ ቆሮንቶስ 6፡14
መ. 1ኛ ጢሞቲዎስ 6፡11
ሠ. 2ኛ ጢሞቲዎስ 2፡22፤ 3፡16
ረ. 1ኛ ዮሐንስ 3፡7
ሰ. 1ኛ ጴጥሮስ 2፡24
6. እግዚአብሔር ዓለምን በጽድቅ ይፈርዳል
1. ሐዋ. 17፡31
2. 2ኛ ጢሞቲዎስ 4፡8
ጽድቅ የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው፣ በክርስቶስ በኩል ለኃጢአተኛው የሰው ልጅ በነጻ የተሰጠ። እሱም
ሀ. የእግዚአብሔር ደንብ
ለ. የእግዚአብሔር ስጦታ
ሐ. የክርስቶስ ድርጊት ነው።

ነገር ግን እሱ ደግሞ ጻድቅ የመሆን ሂደት፣ ያም በጽናት እና በብርታት መያዝ ያለበት ነው፤ አንድ ቀን በክርስቶስ ዳግም ምጽዓት የምንቀዳጀው። ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረት በደኅንነት ይመለሳል፣ ነገር ግን ሂደቱ በሕይወት ዘመን ሁሉ ፊት ለፊት ይገኛል በሞት ወይም <u>በፓሮሲያ!</u>

እዚህ መልካም ጥቅስ አለ፣ *ከጳውሎስና ጸሑፎቹ መዝገበ ቃላት* የተጠቀሰ አይ ቪ ፒ

"ካልቪን፣ ከሉተር ከፍ ባለ መልኩ አጽንዖት የሚሰጠው ግንኙነታዊ በሆነው የእግዚአብሔር ጽድቅ ገጽታ ላይ ነው። የሉተር አተያይ በእግዚአብሔር ጽድቅ ላይ፣ ከጥፋተኝነት ነጻ መሆንን ገጽታ የያዘ ይመስላል። ካልቪን አጽንዖት የሚሰጠው የእግዚአብሔርን ጽድቅ ለእኛ ያለውን አስደናቂ አፈጣጠር ከግንኙነት ወይም ከተካፋይነት አኳያ ነው" (ገጽ 834)።

እንደ እኔ የአማኝ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት ሦስት ገጽታዎች አሉት።
1. ወንጌል አካል ነው (የምስራቅ ቤተ ክርስቲያንና የካልቪን አጽንዖት)
2. ወንጌል እውነት ነው (የአውግስጢኖስና የሉተር አጽንዖት)
3. ወንጌል የተለወጠ ሕይወት ነው (የካቶሊክ አጽንዖት)

ሁሉም እውነት ናቸው እናም አንድ ላይ መያዝ ይኖርባቸዋል፣ ለጤናማ፣ ትርጉም ላለው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ክርስትና። ማንም በጣም አጽንዖት ከሰጠ ወይም ካንኳሰሰ ችግሮች ይፈጠራሉ።

ኢየሱስን መቀበል ይኖርብናል!
ወንጌልን ማመን ይኖርብናል!
ኢየሱስን መምሰል ይኖርብናል!

**1፡6 "እግዚአብሔር ያውቃል"** "ያውቃል" የሚለው ቃል ፍችው "የቀረበ ግላዊ ግንኙነት" ነው (ዘፍ. 4፡1፤ ኤር. 1፡5)።

## ልዩ ርዕስ፡ ማወቅ (ባብዛኛው ዘዳግምን እንደ ምሳሌ በመጠቀም)

የዕብራይስጡ ቃል "ማወቅ" (ቢ.ዲ.ቢ. 393) በርካታ ትርጉም አለው (የትርጉም መስኮች) በዓይነቱ።
1. መልካምንና ክፉውን ለመረዳት - ዘፍ. 3፡22፤ ዘዳ. 1፡39፤ ኢሳ. 7፡14-15፤ ዮናስ 4፡11
2. በመረዳት ለማወቅ - ዘዳ. 9፡2፣3፣6፤ 18፡21

3. በልምድ ለማወቅ - ዘዳ. 3:19፤ 4:35፤ 8:2፣3፣5፤ 11:2፤ 20:20፤ 31:13፤ ኢያሱ. 23:14
4. ለመገንዘብ - ዘዳ. 4:39፤ 11:2፤ 29:16
5. በግል ለማወቅ
   ሀ. ግለሰብ - ዘፍ. 29:5፤ ዘጸ. 1:8፤ ዘዳ. 22:2 ፤33:9
   ለ. አምላክ - ዘዳ. 11:28፤ 13:2፣6፣13፤ 28:64፤ 29:26፤ 32:17
   ሐ. ያህዌ - ዘዳ. 4:35፣39፤ 7:9፤ 29:6፤ ኢሳ. 1:3፤ 56:10-11
   መ. ያታዊ - ዘፍ. 4:1፣17፣25፤ 24:16፤ 38:26
6. የቀሰሙት ክህሎት ወይም እውቀት - ኢሳ. 29:11፣12፤ አሞጽ 5:16
7. ጥበበኛ መሆን - ዘዳ. 29:4፤ ምሳ. 1:2፤ 4:1፤ ኢሳ. 29:24
8. የእግዚአብሔር እውቀት
   ሀ. የሙሴ - ዘዳ. 34:10
   ለ. የእስራኤል - ዘዳ. 31:21፣27፣29

⊡ **"የከፉዎች መንገድ ግን ትጠፋለች።"** *ሥነ-መለኮታዊው ጥያቄ "ይጠፋል" ማለት ምን ማለት ነው?* (ቢዲቢ 1፣ ኬቢ 2)

1. አጠቃላይ ሕልውናን ማጣት (ማለትም፣ መደምሰስ)
2. በምድር ላይ አያበቃም (ማለትም፣ ሞት)

ጉዳዩ ጽኑ ሆኗል፣ በዘመናዊው ዘላለማዊ ገሀነም ውይይት። አንዳንድ ወንጌላዊ ሊቃውንት (ማለትም፣ ጆን ስቶት) የፍርድ ጊዜ እንደሚኖር ያቀነቅናሉ፣ ከዚያም ለኃጢአተኞች ሕልውና አይኖራቸውም፣ ከዘላለማዊ ቅጣት ምትክ። የእኔ ችግር፣ ያው ተመሳሳይ ቃል፣ "ዘላለማዊ" ማቴ. 25፡46 ላይ ጥቅም ላይ የዋለው፣ ሁለቱንም "ቅጣት" እና "የፍጻሜአዊ ሕይወት" መግለጹ ነው። ተመስጧዊ ደራሲ እንዴት በተለያዩ መልኮች በአንድ ዓይነት ቁጥር ላይ ሊጠቀም እንደቻለ ሊታየኝ አልቻለም።

## ልዩ ርዕስ፡ ሙታን የት ናቸው?

I. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. ሁሉም ሰዎች ወደ ሲኦል ይወርዳሉ (ከሥርወ ቃል አኳያ ርግጠኛ ያልሆነ፣ ቢዲቢ 1066)፣ እሱም ሞትን የሚያመለክት ወይም መቃብርን፣ ባብዛኛው በጥበብ ሥነ ጽሑፍ እና በኢሳይያስ። በብሉይ ኪዳን፣ ጥላማ፣ ንቁ፣ ነገር ግን ደስታ የሌለበት ሕላዌ ነበር (ኢዮብ 10፡21-22፤ 38፡17፤ መዝ. 107፡10፣14)።
   ለ. ሲኦል በባሕርዩ
      1. ከእግዚአብሔር ፍርድ ጋር ይያያዛል (እሳት)፣ ዘዳ. 32፡22
      2. ከፍርድ ቀን በፊት ካለው ቅጣት ጋር ይያያዛል፣ መዝ. 18፡4-5
      3. ከአባዶን (ጥፋት) ጋር ይያያዛል፣ ነገር ግን ለእግዚአብሔር የታወቀ፣ ኢዮብ 26፡6፤ መዝ. 139፡8፤ አሞጽ 9፡2
      4. ከ "ጉድጓድ" (ከመቃብር) ጋር ይያያዛል፣ መዝ. 16፡10፤ ኢሳ. 14፡15፤ ሕዝ. 31፡15-17
      5. ክፉዎች ከነሕይወታቸው ወደ ሲኦል ይወርዳሉ፣ ዘኁ. 16፡30፣33፤ መዝ. 55፡15
      6. ዘወትር ሰውኛ የሚሆነው አፈ ሰፊ በሆነ እንስሳ ነው፣ ዘኍ. 16፡30፤ ኢሳ. 5፡14፤ 14፡9፤ ዕንባ. 2፡5
      7. ሰዎች እዚያ ሪፋይም ተብለው ይጠራሉ፣ (ኢሳ. 14፡9-11)
II. አዲስ ኪዳን
   ሀ. የዕብራይስጡ ሲኦል በግሪኩ ሀዳስ ነው የሚተረጎመው (ያልታየው ዓለም)
   ለ. ሃዳስ (ሲኦል) በባሕርዩ
      1. ሞትን ያመለክታል፣ ማቴ. 16፡18
      2. ከሞት ጋር ይያያዛል፣ ራዕ. 1፡18፤ 6፡8፤ 20፡13-14
      3. ዘወትር የሚመሰለው የቋሚ ቅጣት ስፍራ ነው (ገሃነም)፣ ማቴ. 11፡23 (የብሉይ ኪዳን ጥቅስ)፤ ሉቃስ 10፡15፤ 16፡23-24
      4. ዘወትር የሚመሰለው ከመቃብር ጋር ነው፣ ሉቃስ 16፡23
   ሐ. ይከፋፈላል (ራቢዎች)
      1. የጻድቃኖች ክፍል ገነት ይባላል (በርግጥ የሰማይ ሌለኛው ስም፣ 2ኛ ቆሮ. 12፡4፤ ራዕ. 2፡7)፣ ሉቃስ 23፡43
      2. የከፉዎች ክፍል እንጦርጦስ ይባላል፣ 2ኛ ጴጥ. 2፡4፣ እሱም ለክፉዎች መላእክት ማቆያ ስፍራ (ዘፍ. 6፤ 1ኛ ሄኖክ)
   መ. ገሃነም
      1. የብሉይ ኪዳንን ሐረግ ያንጸባርቃል፣ "የሄኖም ልጆች ሸለቆ፣" (ከኢየሩሳሌም በስተደቡብ)። እሱም የፍንቄአውያን የእሳት ጣዖት፣ የሞሎክ አምልኮ የሚፈጸምበት (ቢዲቢ 574)፣ የሕጻናት መሥዋዕት የሚቀርብበት ነበር፣ (2ኛ ነገሥ. 16፡3፤ 21፡6፤ 2ኛ ዜና. 28፡3፤ 33፡6)፣ እሱም በሌዋ. 18፡21፤ 20፡2-5 የተከለከለው።
      2. ኤርምያስ እሱን ከጣዖት ማምለኪያነት ወደ ያህዌ የፍርድ ስፍራ ቀይሮታል (ኤር. 7፡32፤ 19፡6-7)። እሱም የእሳት፣ የዘላለም ፍርድ ቦታ ሆኗል፣ 1ኛ ሄኖክ 90፡26-27 እና ሲብ. 1፡103።
      3. በኢየሱስ ጊዜ የነበሩት አይሁድ በአባቶቻቸው የሕጻናት መሥዋዕት ጣዖት አምልኮ በጣም ያፍሩ ስለነበር፣ ስፍራውን ለኢየሩሳሌም የቆሻሻ መጣያ ስፍራ አድርገውታል። አብዛኞቹ የኢየሱስ ዘይቤዎች፣ ስለ ዘላለማዊ ፍርድ የተገኙት ከዚህ ስፍራ (እሳት፣ ጭስ፣ ትሎች፣ ግማት፣ ነው፣ ማርቆስ 9፡44፣46)። ገሃነም የሚለው ቃል በኢየሱስ ብቻ ነው ጥቅም ላይ የዋለው (ከያዕቆብ 3፡6 በቀር)።
      4. የኢየሱስ የገሃነም አጠቃቀም
         ሀ. እሳት፣ ማቴ. 5፡22፤ 18፡9፤ ማርቆስ 9፡43

ለ. ቋሚ፣ ማርቆስ 9፡48 (ማቲ. 25፡46)
ሐ. የጥፋት ስፍራ (የነፍስም የሥጋም)፣ ማቴ. 10፡28
መ. ከሲያል ጋር ትይዩ ነው፣ ማቴ. 5፡29-30፤ 18፡9
ሠ. ከፉዎችን "የሲኦል ልጆች" በሚያስብል ባሕርይ፣ ማቴ. 23፡15
ረ. የፍርድ ውሳኔ ውጤት፣ ማቴ. 23፡33፤ ሉቃስ 12፡5
ሰ. የገሃነም ጽንሰ ሐሳብ የሁለተኛ ሞት ትይዩ ነው (ራዕ. 2፡11፤ 20፡6፣14) ወይም የእሳት ባሕር (ማቴ. 13፡42፣50፤ ራዕ. 19፡20፤ 20፡10፣14-15፤ 21፡8)። እሱም ማለት የሚቻለው የእሳት ባሕር የሰዎች ቋሚ መኖርያ ስፍራ ተደርጎ ነው (ከሲያል) እንዲሁም ክፉ መላእክት (ከእንጦርጦስ፣ 2ኛ ጴጥ. 2፡4፤ ይሁዳ 6 ወይም ጥልቁ፣ ሉቃስ 8፡31)፤ ራዕ. 9፡1-10፤ 20፡1፣3)።
ሸ. ለሰዎች አልተሠራም ነበር፣ ነገር ግን ለሰይጣንና ለመላእክቱ፣ ማቴ. 25፡41
ሠ. በሲያል፣ በሀዳስ፣ እና በገሃነም መካከል መነባበር ስላለ ማለት የሚቻለው፣
1. በዋነኛነት ሁሉም ሰዎች ወደ ሲያል/ሀዳስ ይወርዳሉ
2. እዚያም ያደረጉት ሥራ (መልካም ቢሆን ክፉ) ከፍርድ ቀን በኋላ ይብስባቸዋል፣ ነገር ግን የክፉዎች ስፍራ እንደዛው ይቀራል (በዚህን ምክንያት ነው ኪጀት ሃዳስን ሲተረጉም (መቃብር) ገሃነምን (ሲያል) ያለው።
3. የአኪ ጽሑፍ ብቻ ነው ከፍርድ ቀን በፊት ያለው እሳት ምሳሌ መሆኑን የገለጠው፣ የሉቃስ 16፡19-31 (አልአዛርና ሃብታሙ ሰው)። ሲኦል ደግሞ እንደ አሁኑ ቅጣት ስፍራ ተገልጧል፣ (ዘዳ. 32፡22፤ መዝ. 18፡1-5)። ሆኖም፣ ማንም በምሳሌ ላይ መሠረተ እምነቱን አይጥልም።

III. በሞትና በትንሣኤ መካከል ያለ ማዕከላዊ ስፍራ
ሀ. አኪ "የነፍስን መዋቲነት" አያስተምርም፣ እሱም ከበርካታ ጥንታዊ የከሕይወት በኋላ አመለካከቶች አንዱ የሆነው።
1. የሰዎች ነፍሳት ከሥጋዊ አካል በፊት ነበር
2. የሰዎች ነፍሳት ከሥጋዊ ሞት በፊትም ሆነ በኋላ ዘላለማዊ ናቸው
3. ሥጋዊ አካል የሚታየው እንደ እስር ቤት ሲሆን፣ ሞት ደግሞ ወደ ቅድመ ተፈጥሮ ተፈትቶ መመለስ ነው
ለ. አኪ ከአካሉ ስለ ተለየ ሕይወት፣ በሞትና በትንሣኤ መካከል ስላለው ፍንጭ ይሰጣል
1. ኢየሱስ በሥጋና በነፍስ መካከል ስላለው ክፍል ተናግሯል፣ ማቴ. 10፡28
2. አብርሃም አሁን ምናልባት አካል ሊኖረው ይችላል፣ ማርቆስ 12፡26-27፤ ሉቃስ 16፡23
3. ሙሴና ኤልያስ በመለወጥ ጊዜ ሥጋዊ አካል ነበራቸው፣ ማቲ. 17
4. ጳውሎስ የሚለው በዳግም ምጽአት በኢየሱስ ያሉት ነፍሳት በመጀመሪያ አዲሱን አካላቸውን ይይዛሉ፣ 2ኛ ተሰ. 4፡13-18
5. ጳውሎስ የሚለው አማኞች አዲሱን መንፈሳዊ አካል በትንሣኤ ቀን ያገኛሉ፣ 1ኛ ቆሮ. 15፡23፣52
6. ጳውሎስ የሚለው አማኞች ወደ ሲያል አይወርዱም ነው፣ ነገር ግን በሞት ከኢየሱስ ጋር ይሆናሉ፣ 2ኛ ቆሮ. 5፡6፣8፤ ፊሊጵ. 1፡ 23። ኢየሱስ ሞትን ድል ነሥቷል፣ እናም ጻድቁን ከእሱ ጋር ወደ ሰማይ ይወስደዋል፣ 1ኛ ጴጥ. 3፡18-22።

IV. ሰማይ
ሀ. ይህ ቃል በመጽሐፍ ቅዱስ በሦስት መልኩ ጥቅም ላይ የሚውል ነው።
1. ከመሬት በላይ ያለው ከባቢ ዓየር፣ ዘፍ. 1፡1፣8፤ ኢሳ. 42፡5፤ 45፡18
2. ከዋክብታማ ሰማይ፣ ዘፍ. 1፡14፤ ዘዳ. 10፡14፤ መዝ. 148፡4፤ ዕብ. 4፡14፤ 7፡26
3. የእግዚአብሔር ዙፋን ስፍራ፣ ዘዳ. 10፡14፤ 1ኛ ነገሥ. 8፡27፤ መዝ. 148፡4፤ ኤፌ. 4፡10፤ ዕብ. 9፡24 (ሦስተኛው ሰማይ፣ 2ኛ ቆሮ. 12፡2)
ለ. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከሕይወት በኋላ ብዙም አይገልጽ። ምናልባትም የወደቀው ሰው ነገሩን የመረዳት መንገዱም ሆነ አቅሙ ስለሌለው ይሆናል፣ (1ኛ ቆሮ. 2፡9)።
ሐ. ሰማይ ስፍራም (ዮሐንስ 14፡2-3) እንዲሁም አካል ነው፣ (2ኛ ቆሮ. 5፡6፣8)። ሰማይ ምናልባት የኤደን ገነት መመለስ ይሆናል፣ (ዘፍ. 1-2፤ ራዕይ 21-22)። ምድር ትጸዳለች ትታደሳለችም (ሐዋ. 3፡21፤ ሮሜ 8፡21፤ 2ኛ ጴጥ. 3፡10)። የእግዚአብሔር አምሳል (ዘፍ. 1፡26-27) በክርስቶስ ተመልሷል። አሁን የኤድን ገነት ወዳጃዊ ኅብረት ዳግም ተችሏል።

ሆኖም፣ ይህ ዘይቤአዊ ነው፣ (ሰማይ፣ እንደ ግዙፍ፣ ኩብ ከተማ የራዕይ 21፡9-27) እናም በጥሬ ቃሉ አይደለም። 1ኛ ቆሮንቶስ 15 የሚገልጸው የሥጋዊ አካልንና የመንፈሳዊ አካልን ልዩነት፣ እንደ ትልቅ ተክል ዘር አድርጎ ነው። ደግሞም 1ኛ ቆሮ. 2፡9 (ከኢሳ. 64፡4 እና 65፡17 የተጠቀሰ) ታላቅ ቃል ኪዳንና ተስፋ ነው! እሱን ስናየው እሱን እንደምንመስል አውቃለሁ፣ (1ኛ ዮሐንስ 3፡2)።

V. የመርጃ ምንጮች
ሀ. ዊሊየም ሄንድሪክሰን፣ *መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ከዚህ ሕይወት በኋላ*
ለ. ማውሪክ ራውሊንግስ፣ *ከሞት ደጆ ባሻገር*

# የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "ሁለቱ መንገዶች" የሚለው ሐረግ ምን ማለት ነው?

2. ከዚህ መዝሙር ላይ በጻድቅ ሰውና በክፉ ሰው መካከል ያለውን ልዩነት ግለጽ።
3. የዘይቤዎቹን አጠቃቀም አብራራ
   ሀ. መራመድ... መንገድ
   ለ. ዛፍ
   ሐ. ትቢያ
4. መዝሙሩ የሚያስተምረው የፍጻሜውን ፍርድ ነው ወይስ ጊዜያዊውን ፍርድ?
5. ይህ መዝሙር ከኢዮብ፣ ወይም ከመዝሙር 37 እና 73 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
6. ይህ መዝሙር ለሙሉው መዝሙር እንደ መግቢያ እንዴት ይወሰዳል?

## መዝሙር 2
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች*

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| በእግዚአብሔር የተቀባው አገዛዝ<br><br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | የመሲሑ ድልና መንግሥት | ጌታ ሁለንተናዊ አገዛዝን ለንጉሡ ይሰጣል (ንጉሣዊ መዝሙር ለንግሥና የተቀነባበረ) | በእግዚአብሔር የተመረጠው ንጉሥ | መሲሐዊ ትዕይንት |
| 2:1-3 | 2:1-3 | 2:1-3 | 2:1-3 | 2:1-3 |
| 2:4-6 | 2:4-6 | 2:4-6 | 2:4-6 | 2:4-6 |
| 2:7-9 | 2:7-9 | 2:7-9 | 2:7-9 | 2:7-9 |
| 2:10-12 | 2:10-12 | 2:10-12ለ | 2:10-12 | 2:10-12 |
| | | 2:12ሐ | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር በአኪ የሚታወቀው በመሲሐዊ ነው (ዕብ. 1:5፤ 5:5፣ ማለትም፣ ልጅ፣ መዝ. 1:7)። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው
ሀ. ጴጥሮስ፣ ሐዋ. 4፡25 ላይ
ለ. ጳውሎስ፣ ሐዋ. 13፡33 ላይ
የዚህ ችግር ኢየሱስን በመጥቀሱ ቁጥር 7 ላይ ነው። "እኔ ዛሬ ወለድኩህ" ከሚለው ጋር የሚዛመደውን ሙሉ ማስታወሻ እዚያ ተመልከት።

ለ. መሲሐዊው አገዛዝ ሁለንተናዊ ይሆናል (ይህም ግልጽ የሆነ መደምደሚያ ነው ለአሀዳዊነት (በአንድ አምላክ ማመን) (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝሙር 2:9፣ መዝ. 2:8፤ ራዕ. 12:5፤ 19:5 ላይ፤ የእኔን የራዕይ ሐተታ www.freebiblecommentary.org ላይ ተመልከት)።

ሐ. "ከአሕዛብ" ተቃዋሚ ይኖራል (ዝከ. 2፡1-3)። ብዙዎቹ ተንታኞች ይሄንን የሚያዛምዱት እንደ መጨረሻው ዘመን ወታደራዊ ግጭት ነው (ማለትም፣ ቅድመ-ሚሊኒየማዊነት) ያህዌንና መሲሑን በሚያውቁት እና በማያውቁት መካከል! ይህም ዘፍጥ. 3፡15 ላይ ያለው ተስፋ እና ራዕይ 21-22 ላይ ያለው አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ቅድጅት ነው። በዚህ መካከል ያለው ሁሉ አስፈሪ የዓመጻ ቅንፍ ነው፣ እግዚአብሔር ከልዕለ-ፍጡሩ ጋር ያለውን የኅብረት ዕቅድ የሚጋፋ (ማለትም፣ 1:26-27፤ 3፡8)።

መ. ግጭት ሊመጣ ይችላል፣ ነገር ግን ያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ አለው፣ መሲሑን የሚያካትት።

## ልዩ ርዕስ፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ

ለእናንተ ለአንባቢዎቼ ግልጽ ማድረግ የሚኖርብኝ በዚህ ነጥብ ላይ ቅድመ-አቋም መያዜን ነው። የእኔ ስልታዊ ሥነ-መለኮት ካልቫኒያዊ አይደለም ወይም ፍጹም ነጻነታዊ፣ ነገር ግን የታላቁ ተልዕኮ ወንጌላዊነት ነው (ማቴ. 28፡18-20፤ ሉቃስ 24:46-47፤ ሐዋ. 1:8)። እኔ የማምነው እግዚአብሔር ሰዎችን ሁሉ ለመዋጀት ዘላለማዊ ዕቅድ እንዳለው ነው (ምሳ.፣ ዘፍ. 3:15፤ 12:3፤ ዘጸ. 19:5-6፤ ኤር. 31:31-34፤ ሕዝቅኤል 18፤ 36:22-39፤ ሐዋ. 2:23፤ 3:18፤ 4:28፤ 13:29፤ ሮሜ. 3:9-18,19-20,21-31)። በአምሳሉና በመልኩ የተፈጠሩትን ሁሉ (ዘፍ. 1:26-27)። ኪዳናቱ በክርስቶስ አንድ ይሆናሉ (ገላ. 3:28-29፤ ቆላ. 3:11)። ኢየሱስ የእግዚአብሔር ምሥጢር ነው፣ ተሸሽጎ የነበረውና አሁን የተገለጠው (ኤፌ. 2:11-3:13)! የአኪ. ወንጌል፣ እስራኤል ሳይሆን፣ የቅዱስ ቃሉ ቁልፍ ነው።

ይህ ቅድመ-መረዳት የቅዱስ ቃሉን ትርጉሞቼን ሁሉ አቅልሚቸዋል። ጽሑፎችን ሁሉ የማነበው በእርሱ ውስጥ ነው! ይኽም በርግጥ ቅድመ-አቋም ነው (ሁሉም ተርጓሚዎች እነርሱ አሏቸው!)፣ ነገር ግን እሱ ከቅዱስ ቃሉ የተገኘ ቅድመ-ግምት ነው።

የዘፍጥረት 1-2 አትኩሮት ያህዌ ስፍራ መፍጠሩን ነው፣ እሱና የእርሱ ልዕለ ፍጡር፣ የሰው-ልጅ ኅብረት የሚያደርጉበት (ዘፍ. 1፡26፣27፤ 3፡8)። ሥጋዊ ፍጥረት ለዚህ በይነ-አካላዊ ለሆነ መለኮታዊ አጀንዳ መድረክ ነው።

1. ቅዱስ አውግስጢኖስ እሱን ባሕርይ ያደረገው መለኮት እንዳበጀው ቀዳዳ ነው፣ በእያንዳንዱ ሰው ላይ፣ እሱም በእግዚአብሔር በራሱ ብቻ ሊሞላ የሚችል።
2. ሲ. ኤስ. ሊዊስ ይሄንን ዓለም የሚጠራው "የተነካ ዓለም" በሚል ነው፣ (ማለትም፣ በእግዚአብሔር ለሰዎች የተዘጋጀ)።

ብኪ. ብዙ ፍንጮች አሉት፣ ለዚህ መለኮታዊ አጀንዳ።

1. ዘፍጥረት 3፡15 የመጀመሪያው ተስፋ ነው፣ ያህዌ የሰው ልጅን እንደማይተወው፣ በዚህ ክፉ የኃጢአትና ዓመጻ ምስቅልቅል። እሱም እስራኤልን የሚጠቅስ አይደለም፣ ምክንያቱም እስራኤልም ሆነ የኪዳን ሰዎች ባለመኖራቸው፣ እስከ አብርሃም መጠራት ድረስ፣ ዘፍጥረት 12 ላይ።
2. ዘፍጥረት 12፡1-3 የያህዌ መነሻ ጥሪና መገለጥ ነው፣ ለአብርሃም፣ ይኸውም ለኪዳኑ ሕዝብ ለእስራኤል የሆነ። በዚህ መነሻ ጥሪ እንኳ ቢሆን፣ እግዚአብሔር ሞላው ዓለምን ይመለከታል። ቁጥር 3ን ተገንዘብ!
3. ዘጸአት 20 ላይ (ዘዳግም 5) ያህዌ ሕጉን ለሙሴ ሰጥቷል፣ የተለየ ሕዝቡን እንዲመራ። ዘጸ. 19፡5-6 ላይ ያህዌ ለሙሴ እንደተገለጠለት፣ ለእስራኤል የሚኖረውን የተለየ ግንኙነት እንዳመለከተው ተገንዘብ። ግን ደግሞ ተገንዘብ፣ እነርሱ እንደ አብርሃም መመረጣቸውን፣ ዓለምን ይባርኩ ዘንድ (ዘጸ. 19፡5፣ "ምድር ሁሉ የእኔ ነውና")። እስራኤል ማለት አሕዛብ ያህዌን እንዲያውቁና ወደ እርሱም እንዲማረኩ ማድረጊያ ዘዴ ነበር። በሚያሳዝን መልኩ እነርሱ አልቻሉም (ሕዝ. 36፡27-38)።
4. መዝሙር — 22:27-28፤ 66:4፤ 86:9 (ራዕ. 15:4)
5. በነቢያት በኩል ያህዌ ሁለንተናዊ የመዋጀት ዕቅዱን መግለጡን ቀጥሏል።
   ሀ. ኢሳይያስ – 2:2-4፤ 12:4-5፤ 25:6-9፤ 42:6,10-12፤ 45:22፤ 49:5-6፤ 51:4-5፤ 56:6-8፤ 60:1-3፤ 66:18,23
   ለ. ኤርምያስ – 3:27፤ 4:2፤ 12:15-16፤ 16:19
   ሐ. ሚኪያስ 4:1-3
   መ. ሚልክያስ 1:11

ይህም ሁለንተናዊ አጽንዖት በ ለ ተመቻችቷል፣ "የአዲስ ኪዳኑ" መድረስ (ኤር. 31:31-34፤ ሕዝ. 36:22-38) እሱም በያህዌ ምሕረት ላይ የሚያተኩር፣ በወደቁት ሰዎች ላይ ሳይሆን። "አዲስ ልብ፣" "አዲስ ሐሳብ፣" እና "አዲስ መንፈስ" አለ። መታዘዝ ዋነኛ ነው፣ ግን እሱ ውስጣዊ ነው፣ ዘላለማዊው ሕግ ብቻ ሳይሆን (ሮሜ. 3፡21-31)።

አኪ. በግልጽ አጠናክሮ ያስቀምጣልሁለንተናዊውን የመዋጀት ዕቅድ፣ በብዙ መንገዶች።

1. ታላቁ ተልዕኮ – ማቴ. 28:18-20፤ ሉቃስ 24:46-47፤ ሐዋ. 1:8
2. የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ (ማለትም፣ ዕጣ-ፈንታ) – ሉቃስ 22:22፤ ሐዋ. 2:23፤ 3:18፤ 4:28፤ 13:29
3. እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እንዲድኑ ይሻል – ዮሐንስ 3:16፤ 4:42፤ ሐዋ. 10:34-35፤ 1 ጢሞ. 2:4-6፤ ቲቶ 2:11፤ 2 ጴጥ. 3:9፤ 1 ዮሐንስ 2:2፤ 4:14
4. ክርስቶስ ብኪ. እና አኪን አዋሕዷል – ገላ. 3:28-29፤ ኤፌ. 2:11-3:13፤ ቆላ. 3:11። የሰዎች ማሰናከያዎች እና ልዩነቶች ሁሉ በክርስቶስ ተወግደዋል። ኢየሱስ "የእግዚአብሔር ምሥጢር" ነው፣ ተሸሽጎ የነበረ፣ አሁን ግን የተገለጠ (ኤፌ. 2:11-3:13)።

አኪ. የሚያተኩረው በኢየሱስ ላይ ነው፣ በእስራኤል ሳይሆን። ወንጌል፣ ብሔራዊነት ወይም መልከዓ-ምድራዊ ክልል ሳይሆን፣ ማዕከላዊ ነው። እስራኤል የመጀመሪያው መገለጥ ነበር፣ ኢየሱስ ግን የመዳረሻው መገለጥ ነው (ማቴ. 5፡17-48)።

ተስፋ አለኝ፣ ጊዜ ወስደው ልዩ ርዕሱን እንደሚያነቡት፡ ለምንድነው የብኪ. የኪዳን ተስፋዎች ከአኪ. የኪዳን ተስፋዎች እጅግ የተለዩ የሚመስሉት። እሱንም ቀጥታ የዌብ ሳይት መስመር ላይ ሊያገኙት ይችላሉ www.freebiblecommentary.org።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 2፡1-3**

**[1]አሕዛብ ለምን ያጕረመርማሉ?**
**ወገኖችስ ለምን ከንቱን ይናገራሉ?**
**[2]የምድር ነገሥታት ተነሡ፥**
**አለቆችም በእግዚአብሔርና በመሢሑ ላይ**
**እንዲህ ሲሉ ተማከሩ።**
**[3]ማሰርያቸውን እንበጥስ፥**
**ገመዳቸውንም ከእኛ እንጣል።**

**2፡1-3** ይህ የሚገልጸው የወደቀውን ሰው መንፈስ እንደፈለገው መሆንን ነው (በተለይም፣ ቁ. 3፤ ዘፍጥረት 3)። ብሔራዊነት እግዚአብሔር የሰው ልጆችን የሚጠብቅበት መንገድ ነው፣ ከአንድ የዓለም መንግሥት (ዘፍጥረት 10-11፤ 2 ተሰሎንቄ 2)። ሆኖም፣ አንድ ቀን ዓለም በእግዚአብሔር መሢሕ ሥር አንድ ትሆናለች። ለቤተ-ክርስቲያን ይህ የባብኤል ግንብ የተገላቢጦሽ በጰንጠቆስጤ ተከስቷል (ሐዋ. 2፣ ማለትም፣ "ሁሉም በራሳቸው ቋንቋ ወንጌልን ይሰሙ ነበር")።

**2፡1** ኤቢ (ገጽ 6) ይህን ቀዳሚ ቁጥር የሚተረጉመው፣ "አሕዛብ ለምን ተማከሩ፣ ሕዝቦችስ ሠራዊታቸውን ለምን ቆጠሩ?" በሚል ነው። ይህ ምንባብ የተመሠረተው

1. ትይዩነት
2. የዑጋሬታዊ የቃላት አጠቃቀም
3. ቀዳሚው ግሥ ("መጯጯኽ፣" ቢዲቢ 921፣ ኬቢ 1189፣ ቃል የተጠናቀቀ) እዚህ ብቻ ነው የሚገኘው በብኪ
4. የሥሩ አጠቃቀም፣ "ከንቱ ነገር፣" ריק (ቢዲቢቢዲቢ 937) ዘፍ. 14:14 ላይ፣ በLXX የተተረጎመው (ማለትም፣ "እሱ የራሱን ተከታዮች ቆጠረ" በሚል ነው።

እሱም የተሻለ ትይዩ ከቁጥር 2 ጋር የሚያደርግ ይመስላል።

**2፡2 "*ነገሥታት… ገዥዎች*"** እነዚህም ደግሞ ከመሳ. 5፡3፤ ምሳ. 8፡15 ጋር ትይዩ ናቸው (ቅኔ)።

▣ ***"የምድር"*** "ምድር" የሚለው ቃል ሰፋ ያለ የፍች መስክ አለው። ዐውደ ጽሑፉ ሊወስነው ይገባል፣ እሱ አካባቢያዊ፣ ክልላዊ፣ ወይም ዓለም-አቀፍ ከሆነ። እዚህጋ ጥያቄው "ይህ መዝሙር በቀዳሚነት የሚጠቅሰው እስራኤልን የከበቡትን አገሮች ነው፣ *ጥቅም* (*ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ*)፣ ወይስ ሁሉንም አገሮች (ዝከ. ቁ. 8)"? በአገባቡ ይህ ባለ ብዙ ፍጻሜ ትንቢት ነው፣ እንደ ኢሳ. 7፡14 ወይም ዐቢይ-ምድባዊ እንደ መዝሙር 22። በዚህ መዝሙር የአኪ አጠቃቀም አኳያ፣ እሱ ሁለንተናዊ መልክ ይኖረዋል (ማለትም፣ መሢሐዊ፣ የፍጻሜ መዳረሻ፣ ዓለም-አቀፋዊ)።

አጠቃቀም ነው፣ በደስታና በበዓል ጊዜ /ኢሳ. 53፡11/፡፡

### ልዩ ርዕስ፡ መሬት፣ አገር፣ምድር

እንደ ሁሉም የዕብራይስጥ ሥሮች፣ ዐውደ-ጽሑፍ ዋነኛ ነው ተገቢውን ትርጓሜ ለመወሰን። የተወሰነ ቁጥር ያላቸው የዕብራይስጥ ሥሮች (ማለትም፣ ጥንታዊ ሴማዊ ቋንቋ) በተለያዩ ፍችዎች እና ትርጉሞች እንዲሠሩ አድርጓቸዋል። ይሄኛው ሥር (ቢዲቢ 75፣ ኬቢ 90) ሊሆን የሚችለው

1. ሞላው ዓለም (ምንም እንኳ የጥንቶቹ መጠኑንና ቅርጹን ባይገነዘቡትም። እሱም ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ስለ "ሚታወቀው ዓለም" ነው)
   ሀ. ዘፍጥረት 1-2፤ 6-9፤ 10:32፤ 11:1,4,8,9፤ 14:19፤ 18:18,25፤ 22:18, ወዘተ.
   ለ. ዘጸአት 9:29፤ 19:5
   ሐ. መዝሙር 8:1,9፤ 24:1፤ 47:2,7፤ ኤር. 25:26,29,30
   መ. ምሳሌ 8:31
   ሠ. ኢሳይያስ 2:19,21፤ 6:3፤ 11:4,9,12፤ 12:5
2. ምድር ከሰማይ ጋር ተነጻጽሯል
   ሀ. ዘፍጥረት 1:2
   ለ. ዘጸአት 20:4
   ሐ. ዘዳግም 5:8፤ 30:19
   መ. ኢሳይያስ 37:16
3. በምድር ላይ ለሰው ማደርያ ዘይቤ
   ሀ. ዘፍጥረት 6:11፤ 11:1

ለ. 1 ነገሥት 2:2፤ 10:24
ሐ. ኢዮብ 37:12
መ. መዝሙር 33:8፤ 66:4

4. አገር ወይም ግዛት
ሀ. ዘፍጥረት 10:10,11፤ 11:28,31
ለ. በተለይ፣ እስራኤል (የያህዌ ስጦታ፣ የእርሱ ሀብት)
5. አፈር፣ ኢያሱ 7:21
6. ከምድር በታች (ኬቢ 91)
ሀ. ዘጸአት 15:12
ለ. መዝሙር 22:29፤ 71:20፤ ኤር. 17:13፤ ዮናስ 2:6
7. አዲስ ዓለም
ሀ. ኢሳየያስ 9:1-7፤ 65:17፤ 66:22
ለ. አኪ. ተመልከት፣ሮሜ. 8:19-22፤ ገላ. 6:15፤ 2 ጴጥ. 3:13፤ ራዕ. 21:1,5

ዐውደ-ጽሑፍ፣ ዐውደ-ጽሑፍ፣ ዐውደ-ጽሑፍ ወሳኝ መሆኑን አስታውስ። ተዛማጅ ሥሮች ዘወትር ሊረዱ ይችላሉ፣ ሁልጊዜ ግን አይደለም።

▣ **"ጌታ"** ይህ ለእስራኤል መለኮት (አምላክ) የኪዳን ስም ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 1፡1 ላይ።

▣ **"የተቀባ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ነው፣ "ለመሢሕ።" እሱም ወደ ግሪክ "ክርስቶስ" በሚል ተተርጉሟል። እሱም የመንፈስ ቅዱስን ልዩ መገኘት ተምሳሌት ይሆናል፣ እግዚአብሔር የሰጠውን ተግባር በሰው በኩል ለመፈጸም (1 ሳሙ.10:1፣6፤ 16:13፤ 1 ነገ. 19:16፤ ኢሳ. 61:1)።

## ልዩ ርዕስ፡ መሲሕ

ይህ የተወሰደው ከእኔ ሐተታዊ ማስታወሻ ከዳንኤል 9፡8 ላይ ነው። ይሄንን ቁጥር ለመተርጎም ያለው አስቸጋሪነት ምክንያቱ፣ መሲሕ ወይም የተቀባው ለሚለው ቃል ተያያዥ የሆኑት ታሳቢ ፍችዎች ናቸው (ቢዲቢ 603)።

1. ለአይሁድ ነገሥታት ጥቅም ላይ ውሏል (ምሳ. 1ኛ ሳሙ. 2፡10፤ 12፡3)
2. ለአይሁድ ካህናት ጥቅም ላይ ውሏል (ምሳ. ሌዋ. 4፡3፣5)
3. ለሳይረስ ጥቅም ላይ ውሏል (ኢሳ. 45፡1)
4. ቁ. 1 እና 2 በመዝሙር 110 እና ዘካርያስ 4 ላይ ተደባልቀዋል
5. ለእግዚአብሔር ልዩ ምጽዓት ጥቅም ላይ ውሏል፣ ዳዊታዊ ንጉሥ አዲሱን የጽድቅ ዘመን ለማምጣት
   ሀ. የይሁዳ የዘር ሐረግ (ዘፍ. 49፡10)
   ለ. የእሴይ ቤት (2ኛ ሳሙ. 7)
   ሐ. አጠቃላይ ግዛት (መዝ. 2፤ ኢሳ. 9:6፤ 11:1-5፤ ሚክ. 5:1-4)

እኔ በበኩሌ የተማረከሁት የተቀባው አንዱን ለመለያነት በሚለው ነው፣ እሱም ለናዝሬቱ ኢየሱስ ምክንያቱም

1. ለዘላለማዊ መንግሥት መቅድም፣ በምዕራፍ ሁለት በአራተኛው ኢምፓየር (ግዛት)
2. "ለሰው ልጅ" መቅድም በ7፡13 ዘላለማዊ መንግሥት የተሰጠው
3. የመቤዣ ሐረጎች 9፡24፣ እሱም የሚያመለክተው ወደ ወደቀው ዓለም ታሪክ ድምዳሜ
4. የኢየሱስ የዳንኤልን መጽሐፍ አጠቃቀም፣ በአኪ. (ማቴ. 24:15፤ ማርቆስ 13:14)

## ልዩ ርዕስ፡ የሚመጣው ልዩው መጠሪያዎች

ሀ. ነቢይ – ዘዳ. 18:15,18
ለ. ንጉሥ
1. ከይሁዳ ነገድ፣ ዘፍ. 49:10፤ መዝ. 60:7፤ 108:8
2. ከዳዊት ወገን፣ 2 ሳሙኤል 7 (ከኢሴይ፣ ኢሳ. 11:1)
3. ከሌሎች ጽሑፎች፣ 1 ሳሙ. 2:10፤ መዝ. 89:3-4፤ ኢሳ. 9,11፤ ኤር. 30:8-9፤ ሕዝ. 37:21-22፤ ዘካ. 9:9-10

ሐ. ንጉሥ/ካህን
1. መዝሙር 110 (ንጉሥ፣ ቁ. 1-3፤ ካህን፣ ቁ. 4)

2. ዘካ. 4፡14 (ሁለቱ የወይራ ዛፎች፣ ሁለቱ የተቀቡት ሰዎች፣ ዘሩባቤል [የዳዊት ዘር] እና ኢያሱ [የአሮን ዘር])

መ. የተቀባው (መሢሕ)

1. የእግዚአብሔር ንጉሥ፣ መዝ. 2፡2፤ 45፡7
2. የመንፈስ መገኘት፣ ኢሳ. 11፡2፤ 61፡1
3. የሚመጣው፣ ዳን. 9፡26
4. ሦስት የብኪ መሪዎች ተቀብተዋል፣ ለእግዚአብሔር ጥሪና ኃይልን መታጠቅ ተምሳሌትነት፡ ነገሥታት (ዘጸ. 28:41፤ ሌዋ. 4:3፤ 6:22) እና ነቢያት (1 ነገሥ. 19:16)

ሠ. የንጉሥ ልጅ

1. መዝ. 2፡7፣12
2. የእስራኤል ንጉሥ እንደ እግዚአብሔር ገዥነት ተምሳሌት (1 ሳሙኤል 8)

ረ. የሰው ልጅ (ዳን. 7፡13)

1. ሰው፣ መዝ. 8፡4፤ ሕዝ. 2፡1
2. መለኮት፣ ዳን. 7፡13

ሠ. የተለየ የመዋጀት መጠሪያዎች

1. መከራን የሚቀበል አገልጋይ፣ ኢሳ. 52:13-53:12
2. መከራን የሚቀበል እረኛ፣ ዘካ. 12-14
3. የማዕዘን ደንጊያ፣ መዝ. 118: ኢሳ. 8:14-15፤ 28:16
4. የተለየ ልጅ፣ ኢሳ. 7:14፤ 9:6-7፤ ሚኪ. 5:2
5. ቅርንጫፍ፣ኢሳ. 4:2፤ 11:5፤ 53:2፤ ኤር. 23:5-6፤ 33:15፤ ዘካ. 3:8፤ 6:12

አኪ እነዚህን የተበታተኑ ማጣቀሻዎች ወስዶ እንደ እግዚአብሔር የተለየ የመዋጀት ወኪል ይቆጥራቸዋል፣ እናም ኢየሱስን በእግዚአብሔር ተስፋ የሚመጣው ወደሚል ያሳድጋቸዋል (ምሳ. ማቴ. 16፡13-20፤ ዮሐንስ 11፡25-27)። ሁለቱ የመሢሑ ምጽአቶች እነዚህ በርካታ ተግባራት እና መጠሪያዎች አንድ የሚሆኑበት ነው።

በወንጌላት ላይ ላለ ለመልካም ማብራሪያ፣ ስለ ሰው ልጅ ባለሥልጣንነት አልያም መከራ እንደሚቀበል አገልጋይ፣ የጆርጅ ኢ. ላድ፣ *የአዲስ ኪዳን ሥነ-መለኮት፣* ገጽ 149-158 ተመልከት።

**2፡3** ይህ ቁጥር ሁለት ድብልቆች አሉት

1. እንበጥስ — ቢዲቢ 683፣ ኬቢ 736፣ *ፔይል ድብልቅ*፣ ኤር. 5:5
2. እንጣል – ቢዲቢ 1020፣ ኬቢ 1527፣ *ሂፊል ድብልቅ*

የወደቀው ሰው (ግለሰቦችና የተጠናቀሩ ቡድኖች) ከፈጣሪያቸው መለየትን (ነጻነትን) ፈለጉ (ዘፍጥረት 3)።

"ማሰርያ" (ቢዲቢ 64) እና "ገመድ" (ቢዲቢ 721) የሚያመለክቱት እስረኞችን እንደሚያስሩ ነገሮች ነው (እዚህ፣ ዕቃዎች)። እነርሱ (እንደ ወደቁ ሰዎች ሁሉ) የያህዌን ሕግ የሚመለከቱት ነጻነታቸውን እንደሚከለክል ነው፣ እውነታው ግን፣ የእርሱ ሕግ የተበጀው እኛን ደኅነኛ፣ ደስተኛ፣ እና ውጤታማ እንዲያደርገን ነው፣ በወደቀው ዓለም። ሕግጋቱ የወላጅ የፍቅር መመሪያ ናቸው፣ ምሪትንና ጥበብን የሚሰጡ!

***መዝሙር ፡ 2፡4-6***

**4 በሰማይ የሚኖር እርሱ ይሥቃል፥**
**ጌታም ይሣለቅባቸዋል።**
**5 በዚያን ጊዜ በቍጣው ይናገራቸዋል፥**
**በመዓቱም ያውካቸዋል።**
**6 እኔ ግን ንጉሤን ሾምሁ**
**በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ።**

**2፡4-6** ይህ የሚገልጸው የያህዌን ሐሳብና ድርጊት ነው፣ በአሕዛብ ጩኸት ላይ። ይህ የሰዋዊ ዘይቤ ቋንቋ ነው።

1. ይቀመጣል
2. ይስቃል (መዝ. 59፡8፤ ምሳ. 1፡26)
3. ይሳለቃል
4. በቁጣ ይናገራቸዋል

የወደቀው፣ የተሰባሰበው ሰው የያህዌን ፍቃድ መጋፋት ይችላልን (ማለትም፣ ዘፍጥረት 10-11)? አይችልም!

## ልዩ ርዕስ፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ተገልጧል (አንትሮፖሞርፊያዊ ቋንቋ)

I. ይህ ዓይነቱ ቋንቋ በብሉይ ኪዳን በጣም የተለመደ ነው (ጥቂት ምሳሌዎች)

ሀ. የሥጋዊ አካል ክፍሎች

1. ዓይኖች - ዘፍ. 1፡4፣31፤ 6:8፤ ዘጸ. 33:17፤ ዘኍ. 14:14፤ ዘዳ. 11:12፤ ዘካ. 4:10
2. እጆች - ዘጸ. 15:17፤ ዘኁ. 11:23፤ ዘዳ. 2:15
3. ክንድ - ዘጸ. 6:6፤ 15:16፤ ዘዳ. 4:34፤ 5:15፤ 26:8
4. ጆሮዎች - ዘኍ. 11:18፤ I ሳሙ. 8:21፤ II ነገሥ. 19:16፤ መዝ. 5:1፤ 10:17፤ 18:6
5. ፊት - ዘጸ. 33:11፤ ዘኁ. 6:25፤ 12:8፤ ዘዳ. 34:10
6. ጣት - ዘጸ. 8:19፤ 31:18፤ ዘዳ. 9:10፤ መዝ. 8:3
7. ድምፅ- ዘፍ. 3:8፣10፤ ዘጸ. 15:26፤ 19:19፤ ዘዳ. 26:17፤ 27:10
8. እግሮች - ዘጸ. 24:10፤ ሕዝ. 43:7
9. በሰው መልክ - ዘጸ. 24:9-11፤ መዝ. 47፤ ኢሳ. 6:1፤ ሕዝ. 1:26
10. የእግዚአብሔር መልአክ - ዘፍ. 16:7-13፤ 22:11-15፤ 31:11፣13፤ 48:15-16፤ ዘጸ. 3:4፣13-21፤ 14:19፤ መሳ. 2:1፤ 6:22-23፤ 13:3-22

ለ. ሥጋዊ ድርጊቶች

1. የተፈጥሮ አድራጊ እንደሆነ የተናገረው - ዘፍ. 1:3፣6፣9፣11፣14፣20፣24፣26
2. መራመድ (ማለትም፣ ድምፁ) በዔድን - ዘፍ. 3:8፤ ሌዋ. 26:12፤ ዘዳ. 23:14
3. የኖኅን መርከብ በሩን መዝጋቱ - ዘፍ. 7:16
4. መሥዋዕቱን ማሽተቱ - ዘፍ. 8:21፤ ዘጸ. 29:18፣25፤ ሌዋ. 26:31
5. መውረድ - ዘፍ. 11:5፤ 18:21፤ ዘጸ. 3:8፤ 19:11፣18፣20
6. ሙሴን መቅበሩ - ዘዳ. 34፡6

ሐ. ሰብዓዊ ስሜቶች (ጥቂት ምሳሌዎች)

1. መቆጨት/መጸጸት - ዘፍ. 6:6፣7፤ ዘጸ. 32:14፤ መሳ. 2:18፤ I ሳሙ. 15:29፣35፤ አሞጽ 7:3፣6
2. መበሳጨት - ዘጸ. 4:14፤ 15:7፤ ዘኍ. 11:10፤ 12:9፤ 22:22፤ 25:3፣4፤ 32:10፣13፣14፤ ዘዳ. 6:15፤ 7:4፤ 29:20
3. ቅናት - ዘጸ. 20:5፤ 34:14፤ ዘዳ. 4:24፤ 5:9፤ 6:15፤ 32:16፣21፤ ኢያሱ. 24:19
4. መጥላት/መጸየፍ - ሌዋ. 20:23፤ 26:30፤ ዘዳ. 32:19

መ. ቤተሰባዊ ቃላት (ጥቂት ምሳሌዎች)

1. አባት
   ሀ. የእስራኤል - ዘጸ. 4:22፤ ዘዳ. 14:1፤ ኢሳ. 1:2፤ 63:16፤ 64:8
   ለ. የንጉሥ - II ሳሙ. 7:11-16፤ መዝ. 2:7
   ሐ. ለአባታዊ ድርጊት ዘይቤ - ዘዳ. 1:31፤ 8:5፤ መዝ. 27:10፤ ምሳ. 3:12፤ ኤር. 3:4፣22፤ 31:20፤ ሆሴዕ 11:1-4፤ ሚል. 3:17
2. ወላጅ - ሆሴዕ 11፡1-4
3. እናት - መዝ. 27፡10 (በምታጠባ እናት ምሳሌ)፤ ኢሳ. 49:15፤ 66:9-13
4. ወጣት ታማኝ አፍቃሪ - ሆሴዕ 1-3

II. የዚህን ዓይነት ቋንቋ አጠቃቀም ምክንያቶች

ሀ. ለእግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች መግለጹ አስፈላጊ ስለሆነ። እግዚአብሔርን እንደ ወንድ የመውሰድ ጽንሰ ሐሳብ በስፋት የተሰራጨው የአንትሮፖሞርፊያዊነቱ ምክንያት እግዚአብሔር መንፈስ ስለሆነ ነው!

ለ. እግዚአብሔር ከሁሉ የተሻለ ትርጉም ያለውን የሰው ሕይወት ገጽታዎች ነው የሚወስደው፣ እናም ራሱን ለመግለጫነት ይጠቀምባቸዋል፣ ለወደቀው የሰው ልጅ (አባት፣ እናት፣ ወላጅ፣ አፍቃሪ)

ሐ. ምንም ቢያስፈልግ እንኳ እግዚአብሔር ራሱን በምንም ዓይነት አካላዊ ቅርጽ እንዲወሰን አይሻም (ዘጸዓት 20፤ ዘዳግም 5)

መ. መዳረሻው አንትሮፖሞርፊም የኢየሱስ ሥጋዊነት ነው! እግዚአብሔር ሥጋዊ ሆነ፣ የሚዳሰስ (1ኛ ዮሐንስ 1፡1-3)። የእግዚአብሔር መልእክት የእግዚአብሔር ቃል ሆነ (ዮሐንስ 1:1-18)።

**2፡4 "በሰማይ የሚኖር"** ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ዙፋን ስፍራ ነው፣ የሚገዛበትን! ለ "ሰማይ" ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ ሰማይ

የዕብራይስጡ ቃል (ቢዲቢ 1029፤ ሲተረጎም "ሰማይ፣" "ሰማይ፣" "ጠፈር፣" "አየር" ሲሆን የሚጠቅሰውም በርካታ ነገሮችን ነው (ማለትም፣ ተለጣጣቂ የፍጥረታት ከበቦች ወይም ንፍቆች)፡

1. ዘፍ. 1፡8-20 እሱ የሚጠቅሰው ከምድር በላይ ያለውን ከባቢ አየር ነው፣ ደመናት የሚንቀሳቀሱበትና ወፎች የሚበሩበት።
2. ይህ ከበብ (ዘፍ. 1:6,20፤ ኢሳ. 40:22፤ 42:5) ከምድር በላይ ያለው፣ እግዚአብሔር ዝናብ የሚልክበት ነው (ማለትም፣ "የሰማይ መስኮቶች፣" መዝ. 78:23-29፤ ሚል3:10 ወይም "የሰማይ የውኃ ጋኖች፣" ኢዮብ 38:37)።
3. ይህ ከበብ ከዋክብት የሚኖሩበትና ፕላኔቶች የሚንቀሳቀሱበት ነው (ባለ ሁለት ገጽታ (ዳይሜንሽን))። እሱም የኮስሞ ፍጥረታትን ሁሉ ሊያመለክት ይችላል (አስሮች ቢሊዮኖች ፍኖተ-ሐሊብ (ጋላክሲ))።
4. ከዚህ ከበብ በላይ የእግዚአብሔር መኖርያ ነው (ማለትም፣ ሦስተኛው ወይም አራተኛው ሰማይ)። እሱም ከፍተኛው ሰማይ ነው (ምሳ. ዘዳ. 10:14፤ 1 ነገ. 8:27,30,32፤ መዝ. 2:4፤ 148:4፤ ኢሳ. 66:1)።

5. ሥነ-መለኮታዊ አጽንዖቱ
ሀ. እግዚአብሔር የሁሉም ነገር ፈጣሪ ነው።
ለ. እሱ ፍጥረታትን ይቆጣጠራል (ማለትም፣ ብርሃን እና ጨለማ፣ ዝናብ እና ድርቅ)።
ሐ. እሱ ሰማያዊ ብርሃናትን ፈጥሯል፣ አኑሯቸዋልም (ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ፕላኔቶች፣ ተወርዋሪ ከዋክብት)።
መ. የእውነታው ክበቦች ወይም ግዛቶች አሉ፡
1) ምድር
2) ከምድር በላይ
3) የማይታዩ/መልአካዊ (ቆላ. 1፡16)
4) የእግዚአብሔር መገኛ እና መኖርያ
ሠ. እነርሱ ሁሉ በእግዚአብሔር የተገናኙና ቁጥጥር ሥር ናቸው

▣ **"ይስቃል"** ግሡ (ቢዲቢ 965፣ ኬቢ 1315፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) በጥሬው የያህዌን ሉዓላዊነት መግለጫ መንገድ ነው። የዩቢኤስ *ማስታወሻ መጽሐፍ* (ገጽ 26) ይዘታዊ አስተያየት አለው። "መዝ. 1፡1 ላይ 'ዋዘኞች' ማለት በእግዚአብሔር ላይ የሚያላግጡ ሰዎችን ነው፤ እዚህጋ እግዚአብሔር ነው የጣዖት አምላኪ አለቆችን የሚሳለቅባቸው።"

▣ **"ጌታ"** ቁጥር 4ሀ እና 4ለ ትይዩ ናቸው፣ ስለዚህ የተጠቀሰው መለኮት ያህዌ ነው (ዝኪ. ቁ. 2ሐ)። እዚህጋ ቃሉ ያህዌ አይደለም፣ አዶን እንጂ፣ የዕብራይስጥ ቃል "ባለቤት፣" "ባል፣" "ጌታ።" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች መዝ. 1፡1 ላይ።

**2፡6** ያህዌ በተቃርኖ ልዩነት ከጣዖታት፣ ማየት፣ መስማት፣ ወይም መሥራት ከማይችሉ፣ ከተበጁ ("የተለየ፣" ቢዲቢ 651፣ ኬቢ 703፣ *ቃል የተጠናቀቀ*) ንጉሥ! የእስራኤል ንጉሥ እንደ ያህዌ ተወካይ ይሠራል።
ሰዋዊ ተውላጠ ስሞች፣ "እኔን፣" "የእኔ" (ሁለቴ) አጠቃቀማቸውን ተገንዘብ። ያህዌ በአካል በዓለም ላይ ይገኛል፣ ንቁም ነው፣ በተለይም ከኪዳን ሕዝቡ ጋር።

▣ **"በተቀደሰው ተራራዬ በጽዮን ላይ"** እነዚህ ሁለቱም የሚጠቅሱት የሞሪያን ተራራ፣ የኢየሩሳሌምን ኮረብታ ነው፣ መቅደሱ የተሠራበትን። በመነሻው ጽዮን የሚጠቀሰው የኢያቡሳውያን ምሽግ የተሠራበትን ኮረብታ ነው (ማለትም፣ ኢየሩሳሌም በሰባት ኮረብቶች መከበቧ። ዳዊት ድል አድርጎ በኮረብታዋ ላይ ቤተ-መንግሥቱን ሠራ። ኋላ ላይ የሙሉው ከተማ የኢየሩሳሌም መጥሪያ ሆነ።

**መዝሙር ፡ 2፡7-9**
**[7]ትእዛዙን እናገራለሁ**
**እግዚአብሔር አለኝ። አንተ ልጄ ነህ፥**
**እኔ ዛሬ ወለድሁህ።**
**[8]ለምነኝ፥ አሕዛብን ለርስትህ**
**የምድርንም ዳርቻ ለግዛትህ እሰጥሃለሁ።**
**[9]በብረት በትር ትጠብቃቸዋለህ፥**
**እንደ ሸክላ ሠሪ ዕቃዎች ትቀጠቅጣቸዋለህ።**

**2፡7-9** ተናጋሪው አዲስ ንጉሥ ነው፣ እዚህጋ የያህዌ "ልጅ" ይባላል (ዕብ. 1፡2፤ 3፡6፤ 5፡8፤ 7፡28)።

## ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ

ይህ አንደኛው የአዲስ ኪዳን የኢየሱስ መጠሪያ ነው። እሱ በርግጥ መለኮታዊ ፍች አለው። እሱም ኢየሱስን የሚያካትተው እንደ "ልጅ" ወይም "የኔ ልጅ" እና እግዚአብሔርን እንደ "አባት" ነው። እሱ በአዲስ ኪዳን 124 ጊዜ ተከስቷል። የኢየሱስ የገዛ ራሱ መጠሪያ፣ "የሰው ልጅ" እንኳ፣ መለኮታዊ ፍች አለው፣ ከዳን. 7፡13-14።

በብኪ "ልጅ" የሚለው መጠሪያ አራት የተለዩ ምድቦችን ያመለክታል።
ሀ. መላእክት (ዘወትር በብዙ ቁጥር፣ ዘፍ. 6፡2፤ ኢዮብ 1፡6፤ 2፡1)
ለ. የእስራኤል ንጉሥ (II ሳሙ. 7፡14፤ መዝ. 2፡7፤ 89፡26-27)
ሐ. የእስራኤል ሕዝብ በጥቅሉ (ዘጸ. 4፡22-23፤ ዘዳ. 14፡1፤ ሆሴዕ. 11፡1፤ ሚል. 2፡10)
መ. የእስራኤል ፈራጆች (መዝ. 82፡6)

እሱ ሁለተኛው አጠቃቀም ነው፣ ከኢየሱስ ጋር በተያያዘ። በዚህም መልኩ "የዳዊት ልጅ" እና "የእግዚአብሔር ልጅ" ሁለቱም ከII ሳሙኤል 7፤ መዝሙር 2 እና 89 ጋር ይዛመዳል። በብኪ "የእግዚአብሔር ልጅ" ፈጽሞ ጥቅም ላይ አልዋለም በተለይ መሲሕን በተመለከተ፣ እንደ መዳረሻው ንጉሥ እሱም የእስራኤል "የተቀባ ሹም" በቀር። ሆኖም፣ በቀይ ባሕር ጥቅሎች ከመሲሐዊ ማዕርግ ጋር በተያያዘ የተዘወተረ ነው (የተለየውን ዋቢ በኢየሱስና ወንጌላት መዝገበ ቃላት፣ ገጽ 770 ተመልከት)። ደግሞም "የእግዚአብሔር ልጅ"

መሲሐዊ ማዕርግ ነው፣ በሁለቱ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የአይሁድ የምጽዓት የጽሑፎ *ሥራዎች* (II ኢስድራስ 7፡28፤ 13፡32፣37፣52፤ 14፡9 እና ሄኖክ 105፡2)።

የእሱ የአዲስ ኪዳን ዳራ፣ ለኢየሱስ እንደሚያመለክተው በብዙ ምድቦች መልካም ሆኖ ተጠቃሏል።

1. የእሱ ቅድመ-ሕላዌ (ዮሐንስ 1፡1-18
2. የእሱ የተለየ (የድንግል) ልደት (ማቴ. 1፡23፤ ሉቃስ 1፡31-35)
3. ጥምቀቱ (ማቴ. 3፡17፤ ማርቆስ 1፡11፤ ሉቃስ 3፡22። ከሰማይ የመጣው የእግዚአብሔር ድምጽ የመዝሙር 2ን ንጉሥ ነገሥት ከኢሳይያስ 53 መከረራተቀባይ አገልጋይ ጋር ያስተሳስረዋል)።
4. የእሱ የሰይጣን ፈተና (ማቴ. 4፡1-11፤ ማርቆስ 1፡12፣13፤ ሉቃስ 4፡1-13። እሱ ልጅነቱን እንዲጠራጠር ተፈትኗል ወይም ቢያንስ ተግባሩን እስኪያጠናቅቅ ድረስ፣ በተለያየ መልኩ፣ ከመስቀል ይልቅ)።
5. ተቀባይነት በማያገኙ ምስክሮች ለእሱ የተደረገ ማረጋገጫ
   ሀ. አጋንንት (ማርቆስ 1፡23-25፤ ሉቃስ 4፡31-37፣41፤ ማርቆስ 3፡11-12፤ 5፡7)
   ለ. የማያምኑ (ማቴ. 27፡43፤ ማርቆስ 14፡61፤ ዮሐንስ 19፡7)
6. በደቀ-መዛሙርቱ ስለሱ የተደረገ ማረጋገጫ
   ሀ. ማቴ 14፡33፤ 16፡16
   ለ. ዮሐንስ 1፡34፣49፤ 6፡69፤ 11፡27
7. የገዛ ራሱ ማረጋገጫ
   ሀ. ማቴዎስ 11፡25-27
   ለ. ዮሐንስ 10፡36
8. እግዚአብሔርን እንደ አባት የተጠቀመበት ቤተሰባዊ ዘይቤ
   ሀ. "አባ" እያለ ለአግዚአብሔር የተጠቀመበት
      1) ማርቆስ 14፡36
      2) ሮሜ 8፡15
      3) ገላትያ 4፡6
   ለ. በተደጋጋሚ አባት (*patr*) እያለ መጠቀሙ፣ ከመለኮት ጋር ያለውን ዝምድና ለመግለጽ

ለማጠቃለል፣ የ "እግዚአብሔር ልጅ" የሚለው ማዕርግ ታላቅ ሥነ-መለኮታዊ ፍች አለው፣ ብኪን እና የሱን ተስፋ ቃሎችና ምድቦች ለሚያውቁ፣ ነገር ግን የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት የሱን ከአሕዛብ ጋር ያለ አጠቃቀም ይረብሻቸዋል፣ ምክንያቱም ጣዖት አምላኪነት የኋላ ታሪክ ስለነበራቸው፣ የ "አማልክት"፣ እነሱም ሴቶችን ወስደው የዝርያ ውጤት መሆኑን ስለሚቀበሉ፣ ይህም "የተለዩ ሰዎች" ወይም "ኒፊሊም" ስለሚሏቸው።

**2፡7 "እኔ ዛሬ ወለድኩህ"** ይህ ሐረግ ይወክለዋል በሚባለው 2 ሳሙኤል 7 ስሜት (መዝ. 89፡26-27)፣ ያህዌ በዘይቤአዊ ቋንቋ የዳዊት የንግሥና ዝርያ "አባት" መሆኑን ቃል የገባበት። "ዛሬ" የሚያመለክተው የንጉሡን የንግሥና ቀን ነው። ጆን ኤች. ዋልተን፣ *ጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አስተሳሰብና ብኪ፣* ገጽ 89፣ የግርጌ ማስታወሻ 19 ተመልከት፣

"ዘር የመተካቱ ሐሳብ ከተጨባጭ ይልቅ ከሚና ጋር መዛመዱ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ መግለጫዎችም ማስረጃ አለው ... እንደ (መዝ. 2፡7) እዚያም ንጉሡ ለንግሥና ሥልጣኑ የተወለደበት።"

ደግሞም ጂ. ቢ. ኬርድ፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋና ምናባዊነት፣* ገጽ 190 ተመልከት። ሆኖም፣ መዝሙር ላይ ለመሢሑ ነው ጥቅም ላይ የዋለው (ማለትም፣ ኢየሱስ፣ ማቴ. 3፡17፤ ሉቃስ 3፡22፤ ማርቆስ 1፡11፤ 9፡7፤ ሐዋ. 13፡33፤ ዕብ. 1፡5፤ 5፡5)፣ እሱም ተመሳሳይ የሆነ ሥነ-መለኮታዊ ችግሮችን የሚፈጥር፣ በተለይም "ከአሓዳዊነት" ጋር በተያያዘ፣ ኋላ ላይም በአኪ የማደጎአዊነት መናፍቃዊ አስተሳሰብ የሆነ።

## ልዩ ርዕስ፡ አሀዳዊነት

"አሀዳዊነት" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ (አንድ እና አንድ ብቻውን የሆነ አምላክ)፣ እሱም "ከፍ ያለው ጣዖት" ያይደለ፣ የብዝሐዊነት ወይም የኢራናውያን ምንታዌነት (Zoroastrianism) መልካም ጣዖት ያይደለ፣ ይህም ለእስራኤል ልዩ የሆነ (አብርሃም፣ 2000 ዓ.ዓ)። አንድ ብቻ የተለየ በግብፅ እንደነበረ ይገለጻል፣ እምብዛም ያልተለመደ (Amenhotep 4ኛ፣ Akhenaten በመባልም ይታወቃል፣ 1367-1350 ወይም 1386-1361 ዓ.ዓ)።

ይህ ጽንሰ-ሐሳብ በአዲስ ኪዳን በብዙ ሐረጎች ተገልጿል።

1. "እንደ ያህዌ የእኛ ኤሎሂም ያለ የለም፣" ዘጸ. 8፡10፤ 9፡14፤ ዘዳ. 33፡26፤ 1ነገሥ. 8፡23
2. "ከእሱ ውጪ የለም፣" ዘዳ. 4፡35፣39፤ 32፡39፤ 1ሳሚ. 2፡2፤ 2ሳሚ. 22፡32፤ ኢሳ. 45፡21፤ 44፡6፣8፤ 45፡6፣21
3. "ያህዌ አንድ ነው፣" ዘዳ. 6፡4፤ ሮሜ. 3፡30፤ 1ቆሮ. 8፡4፣6፤ 1ጢሞ. 2፡5፤ ያዕቆብ 2፡19
4. "እንዳንተ የለም" 2ሳሚ. 7፡22፤ ኤር. 10፡6
5. "አንተ ብቻህን አምላክ ነህ" መዝ. 86፡10፤ ኢሳ. 37፡16
6. "ከእኔ በፊት አምላክ አልነበረም፣ ከእኔም በኋላ አይኖርም፣" ኢሳ. 43፡10
7. "ሌላ የለም፤ ከእኔ በቀር... ሌላ ምንም የለም፣" ኢሳ. 45፡5፣6፣22
8. "ሌላ ማንም የለም፣ ሌላ አምላክ የለም፣" ኢሳ. 45፡14፣18
9. "ከእኔ በቀር ማንም የለም" ኢሳ. 45፡21
10. "ሌላ የለም፤... እንደኔ ያለ አንድም የለም፣" ኢሳ. 46፡9

ይህ ወሳኝ የሆነ መሠረተ-እምነት በተሻለ መንገድ መገለጡን የግድ መቀበል አለብን። ጥንታውያኖቹ መግለጫዎችን መረዳት የሚኖርብን እንደ “henotheism” ወይም ተግባራዊ አሀድነት ነው (ሌሎች አማልክት አሉ፣ ነገር ግን ለእኛ አንድ አምላክ ነው፣ ዘጸ. 15፡11፤ 20:2-5፤ ዘዳ. 3:28፤ 5:7፤ 6:4፣14፤ 10:17፤ 32:12፤ 1ነገሥ. 8:23፤ Ps. 83:18፤ 86:8፤ 136:1-2)።

ነጠላነትን (አንድነትን) በመግለጽ የሚጀምሩ ቀዳሚዎቹ ጽሑፎች (ፍልስፍናዊ አሀድነት) ጥንታዊ ናቸው (ዘጸ. 8:10፤ 9:14፤ ዘዳ. 4:35፣39፤ 33:26)። ሙሉውና የተጠናቀቀው ጥያቄ በኢሳይያስ 43-46 (ዝከ. 43:11፤ 44:6፣8፤ 45:7፣14፣18፣22፤ 46:5፣9) ላይ ይገኛል።

አዲስ ኪዳን ከዘዳ. 6:4 ከሮሜ. 3:30፤ 1ቆሮ. 8:4፣6፤ ኤፌ. 4:6፤ 1ጢሞ. 2:5፤ እና ያዕቆብ 2:19. ኢየሱስ እንደ ቀዳሚው ትዕዛዝ አድርጎ ጠቅሶታል በማቴ. 22:36-37፤ ማርቆስ 12:29-30፤ ሉቃስ 10:27። ብኪም ሆነ አኪ፣ የሚያስረግጡት የሌሎችን መንፈሳዊ ሕላዌዎች መኖርን ሲሆን (አጋንንት፣ መላእክት)፣ ነገር ግን አንድ ብቸኛ ፈጣሪ/ተቤዢ አምላክ (ያህዌ፣ ዘፍ. 1:1) መሆኑን ነው።

መጽሐፍ ቅዱሳዊው አሀድነት ባሕርይ የሚያደርገው

1. እግዚአብሔር አንድ እና የተለየ ነው (ተዋረዳዊ ሥነ-ሕላዌ እንደሆነ ይታሰባል፣ የተለየ ሳይሆን)
2. እግዚአብሔር አካላዊ ነው (ዘፍ. 1:26-27፤ 3:8)
3. እግዚአብሔር ሥነ-ምግባራዊ (ኢቲካል) ነው (ዘጸ. 34:6፤ ነሀ. 9:17፤ መዝ. 103:8-10)
4. እግዚአብሔር ሰዎችን በራሱ አምሳል ፈጠረ (ዘፍ. 1:26-27) ለኅብረት (ማለትም፣ ቁ. 2)። እሱ ቀናተኛ አምላክ ነው (ዘጸ. 20:2-3

ከአዲስ ኪዳን (አዲስ ኪዳን)

1. እግዚአብሔር ሦስት ዘላለማዊ፣ አካላዊ መገለጫዎች አሉት (ልዩ ርዕስ፡ ሥላሴ 8:11 ተመልከት)
2. እግዚአብሔር በፍጽምናውና በሙላቱ በኢየሱስ ተገልጧል (ዮሐንስ 1:1-14፤ ቆላ. 1:15-19፤ ዕብ. 1:2-3)
3. ለወደቀው ሰው መቤዣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ዕቅድ የአንድያ ልጁ መሥዋዕትነታዊ ስጦታ ነው (ኢሳይያስ 53፤ ማርቆስ 10:45፤ 2ቆሮ. 5:21፤ ፊሊጵ. 2:6-11፤ ዕብራውያን)

ሥነ-መለኮታዊው ጉዳይ “መሢሐዊው ንጉሥ ቅድመ-ሕላዌ መለኮት” ወይስ የተፈጠረ ሕላዌ የሚል ነው (ምሳ. 8፡22-31፤ ሮሜ 1:4)? ዮሐንስ 1:1-3 ለዚህ ጉዳይ መልስ ይሰጣል። እጅግ ጠቃሚ እንዲሆን ከዮሐንስ 1:1-3 ማስታወሻዬ ላካትት።

**ዮሐንስ 1**

**1:1 “በመጀመሪያ”** ይህ የሚያንጸባርቀው ዘፍጥረት 1:1 ሲሆን ደግሞም 1 ዮሐንስ 1:1 ጥቅም ላይ ውሏል፣ ለሥጋዌነት ማጣቀሻ። ሊሆን የሚችለው 1 ዮሐንስ ለወንጌል የመሸኛ መልእክት ነው። ሁለቱም ስለ ግኖስቲሲዝም ይገልጻሉ። ቁጥር 1-5 የሚያጸኑት የኢየሱስ ክርስቶስን ከፍጥረታት በፊት ቅድመ-ሕላዌ መለኮትነት ነው (ዝከ. 1:15፤ 8:56-59፤ 16:28፤ 17:5፤ 2 ቆሮ. 8:9፤ ፊሊ. 2:6-7፤ ቆላ. 1:17፤ ዕብ. 1:3፤ 10:5-8)።

አኪ የሚገለጸው እንደ

1. አዲስ ፍጥረት፣ በውድቀት ምክንያት ነውር የሌለበት (ማለትም፣ ዘፍ. 3:15 ለሰው ልጅ ተፈጽሟል)
2. አዲስ ድል (የተስፋይቱ ምድር)
3. አዲስ ዘጸአት (ነጻ መውጣት) (የተፈጸመ ትንቢት)
4. አዲሱ ሙሴ (ሕግ ሰጭ)
5. አዲሱ ኢያሱ (ዕብ. 4፡8)
6. አዲሱ የውኃ ተአምር (ዕብራውያን 3-4)
7. አዲሱ መና (ዮሐንስ 6)

እና ሌላም ብዙ ተጨማሪ፣ በተለይም ዕብራውያን ላይ።

◘ **“ነበር”** (ሦስቴ) ይህ ያልተጠናቀቀ ጊዜ ነው (ዝከ. ቁ. 1፣2፣4፣10) እሱም የሚያተኩረው ቀጣይነት ባለው ሕላዌ፣ ባለፉት ጊዜያት ላይ ነው። ጊዜው ጥቅም ላይ የዋለው የሎጎስን ቅድመ-ሕላዌ ለማሳየት ነው (ዝከ. 8:57-58፤ 17:5፣24፤ 2ቆሮ. 8:9፤ ቆላ. 1:17፤ ዕብ. 10:5-7)። እሱም ቁ. 3፣ 6 እና 14 ላይ ከሚገኘው የድርጊት ጊዜ ጋር ይቃረናል።

◘ **“ቃል”** የግሪኩ ቃል ሎጎስ የሚጠቅሰው መልእክትን ነው፣ አንድን ቃል ብቻ ሳይሆን። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ግሪኮች የሚጠቀሙበት “የዓለም አስተሳሰብ” የሚለውን ለመግለጽ ነው፣ ዕብራውያን ደግሞ ለ“ጥበብ” ተመሳሳይ። ዮሐንስ ይህን ቃል የመረጠው የእግዚአብሔር ቃል ሁለቱንም አካልና መልእክት መሆኑን ለማስረገጥ ነው። ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ሐ ተመልከት።

◘ **“ከእግዚአብሔር ጋር”** “ከ” “ፊት ለፊት” በሚል ሊታይ ይችላል። እሱም የቅርብ ወዳጅነትን ያሳያል። እሱም ደግሞ ወደ አንድ መለኮታዊ ሕላዌ እና ሦስት አካላዊ ዘላለማዊ መከሰቻዎች ያመለክታል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሥላሴ ዮሐንስ 14፡26 ላይ)። አኪ የሚያስረግጠው ፓራዶክስ (አያዎ) ኢየሱስ ከአብ መለየቱንና ግን ደግሞ ከአብ ጋር አንድ መሆኑን ነው።

◘ **“ቃልም እግዚአብሔር ነበረ”** ይህ ግሥ ያልተጠናቀቀ ጊዜ ነው፣ እንደ ቁ. 1ሀ። ምንም አንቀጽ የለውም (ባለቤቱን የሚገልጽ፣ ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ *ጥያቄና መልሶች፣ ገጽ* 66 ተመልከት) ከ*ቴዎስ* ጋር ነገር ግን*ቴዎስ* በቅድሚያ ነው የተቀመጠው፣ በግሪክ ሐረግ፣ ለአጽንዖት። ይህ ቁጥር እና ቁ. 18 ጠንካራ መግለጫዎች ናቸው ለሎጎስ ፍጹም መለኮትነትና ቅድመ-ሕላዌነት (ዝከ. 5:18፤ 8:58፤ 10:30፤ 14:9፤ 17:11፤ 20:28፤ ሮሜ. 9:5፤ ዕብ. 1:8፤ 2 ጴጥ. 1:1)። ኢየሱስ ፍጹም መለኮት ነው ብሎም ፍጹም ሰው (1 ዮሐንስ 4:1-3)። እሱ እንደ እግዚአብሔር አብ ተመሳሳይ አይደለም፣ ነገር ግን እንደ አብ ተመሳሳይ መለኮታዊ ሕላዌ ነው።

አኪ የሚያስረግጠው የናዝሬቱ ኢየሱስን ፍጹም መለኮትነት ነው፣ ነገር ግን የአብን የተለየ አካልነት ይጠብቃል። አንድ መለኮታዊ ሕላዌ በዮሐንስ 1:1፤ 5:18፤ 10:30፣34-38፤ 14:9-10፤ እና 20:28 ላይ አጽንዖት ሲሰጠው፣ ልዩነታቸው ደግሞ ዮሐንስ 1:2፣14፣18፤ 5:19-23፤ 8:28፤ 10:25፣29፤ 14:11፣12፣13፣16 ላይ አጽንዖት ተሰጥቶታል።

**1፡2** ይህ ከቁ. 1 ጋር ትይዩ ሲሆን፣ እናም በድጋሚ ለኃይለኛው እውነት አጽንዖት ይሰጣል፣ በአህዳዊነት እይታ፣ ኢየሱስ፣ እሱም 6-5 ቅ.ል.ክ አካባቢ የተወለደው ዘወትር ከአብ ጋር ለመሆኑ፣ እናም መለኮት ነው።

**1፡3 "ነገር ሁሉ በእርሱ በኩል የሆነ"** ሎጎስ የአብ የፍጥረት ወኪል ነበር፣ የሚታየውም ሆነ የማይታየው (ዝከ. ቁ. 10፤ 1 ቆሮ. 8:6፤ ቆላ. 1:16፤ ዕብ. 1:2)። ይህም ጥበብ ከተጫወተችው ሚና ጋር ተመሳሳይ ነው መዝ. 33:6 እና ምሳ. 8:12-23 ላይ (ዕብራውያን ላይ "ጥበብ" አንስታይ ጾታ ነው፣ ስም)።

▣ **"ከሆነውም አንዳች ስንኳ ያለ እርሱ አልሆነም"** ይህ የግኖስቲክ የሐሰት ትምህርት መንቀፊያ ነው፣ የመልአካዊ ክልል፣ በከፍተኛው መልካሙ አማልክት እና በአነስተኛው መንፈሳዊ ሕላዌ መካከል፣ ይኸውም ቅድመ-ሕላዌ ነገርን ያደረገ (ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት፣ መ ተመልከት)።

*መገንዘብ የሚኖርበት፣የ"አብ... ወልድ" ምናባዊነት ግላዊ ግንኙነትን የማሳያ ዘይቤአዊ መንገድ መሆኑን ነው* (ዘዳ. 32፡18)። ሰዋዊ ቤተሰብ በቀላሉ የሚረዳው መንገድ ነው፣ ይሄንን ተምሳሌታዊ ኅብረት። ይኸው ተመሳሳይ እውነት ደግሞ "ማወቅ" ለሚለው የዕብራይስጥ ጽንሰ-ሐሳብ ክፋይ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ መዝ. 1፡6 ላይ።

**2፡8** *የመሢሑ ንግሥና ሁለንተናዊ ይሆናል* (መዝ. 67:7፤ ኢሳ. 45:22፤ 52:10፤ ኤር. 16:19፤ ሚክ. 5:4፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር መዝ. 1:2 ላይ)። ይህ የእግዚአብሔር ዓለም ነው። እሱም ለእግዚአብሔርና በአምሳሉ ለተፈጠሩት ሰዎች መንቀሳቀሻ እንዲሆን ነው የተፈጠረው (ዘፍ. 1:26-27) ለኅብረት (ዘፍ. 3:8)። የአዳምና ሔዋን ዓመጸኝነት (ዘፍጥረት 3) የእግዚአብሔርን አምሳያ በሰው ልጅ ጎዳው፣ እንዲሁም ሥጋዊ ፍጥረት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ አሳደረበት (ሮሜ 8፡18-25)። ይህ ዓለም እግዚአብሔር እንዲሆን የፈለገው አይደለም! ሆኖም፣ በሰው ልጅ ላይ ተስፋ ሊቆርጥ ፍቃደኛ አልሆነም። ራሱን በእስራኤል ገልጦ ልጁን ላከ (ዘፍ. 3፡15) ፍጥረትን ወደ ተፈለገበት ዓላማ ለመመለስ። መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረው በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ በገነት መቼት ነው (ዘፍጥረት 1-3፤ መዝ. 1፡3) የሚጨርሰውም በእግዚአብሔርና በሰው ልጅ በገነት መቼት ነው (ራዕይ 21-22)። በዘፍጥረት 3 እና ራዕይ 21-22 መካከል ያለው ሁሉ እግዚአብሔር የተበላሸውን የሚያጸዳበት ነው!

▣ **"ውርስ...ርስት"** እነዚህ ሁለቱም ቃላት ሥነ-መለኮታዊ ጠቀሜታ አላቸው፣ ለእግዚአብሔር ስጦታ፣ ለኪዳኑ ሕዝብ። የመጀመሪያው ዘወትር የሚዛመደው ከሌዋውያን ጋር ነው። ሁለተኛው ለአብርሃም ዝርያዎች የሆነ ተስፋ ነው (ዘፍ. 17:8፤ 48:4፤ ሌዋ. 25:34)።

**2፡9 "በብረት በትር ትጠብቃቸዋለህ"** የዕብራይስጡ ግሥ (ቢዲቢ 949፣ ኬቢ 1270፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*)
ከ רעע ሥር ነው፣ ነገር ግን LXX እና ፔሺታ የሚያነቡት እንደ "መግዛት" ወይም "እረኛ፣" ነው רעה (ቢዲቢ 944)። የጥንቷ ቤተ-ክርስቲያን LXX እና ይህን የምትጠቀመው ሐረጉ ራዕ. 2:27፤ 12:5 and 19:15 ጥቅም ላይ ላይ በዋለበት መልኩ ነው።
ሆኖም፣ በቀጣዩ ስንኝ ላይ ያለው የዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት (ማለትም፣ "መሰባበር" – ቢዲቢ 658፣ ኬቢ 711፣ *ፒይል ያልተጠናቀቀ*) የሚመርጠው "መስበርን" ነው።

▣ **"በትር"** ስሙ (ቢዲቢ 986) ሊሆን የሚችለው "ዱላ፣" "ሽመል፣" ወይም "በትር" ነው። የመጨረሻው አማራጭ የተሻለ ይመስላል፣ በንጉሣዊ ዐውድ አንጻር (መዝ. 45:6፤ 125:3፤ ዘኁ. 24:17፤ ኢሳ. 14:5፤ ሕዝ. 19:11፣14፤ ዘካ. 10:11)። ምንም እንኳ "እረኛ" ትክክል ቢሆንም፣ እንግዲያውስ "በትር" ነው የሚሆነው (መዝ. 23:4፤ ሚኪ 7:14)።

▣ **"እንደ ሸክላ ሠሪ ዕቃዎች ትቀጠቅጣቸዋለህ።"** የሸክላ ዕቃ መስበር በ*ጥቅም* (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) የፍርድ ተምሳሌት ነው።

***መዝሙር ፡ 2፡10-12***

**[10]አሁንም እናንት ነገሥታት፥**
**ልብ አድርጉ እናንት የምድር ፈራጆችም፥ ተገሠጹ።**
**[11]ለእግዚአብሔር በፍርሃት ተገዙ፥**
**በረዓድም ደስ ይበላችሁ።**
**[12]ተግሣጹን ተቀበሉ ጌታ እንዳይቈጣ እናንተም በመንገድ እንዳትጠፉ፥**
**ቍጣው ፈጥና ትነድዳለችና።**
**በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው።**

**2፡10-12** ተለጣጣቂዎቹን ተተኳሪዎችተገንዘቡ፣ እንደ መዝሙረኛ (ማለትም፣ ዳዊት፣ ሐዋ. 4:25)፣ ለያህዌ ሲናገር፣ የዚህን ዓለም ገዥዎች ያስጠነቅቃል፣ እሱን ለመገናኘት እንዲዘጋጁ (ምሳ. 8፡12-21)።

1. ልብ ማለት (ማስተዋል) — ቢዲቢ 968፣ ኬቢ 1328፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
2. ተግሣጽን ተቀበሉ – ቢዲቢ 415፣ ኬቢ 418፣ *ኒፋል ተተኳሪ*
3. ለጌታ ተገዙ – ቢዲቢ 712፣ ኬቢ 773፣ *ቃል ተተኳሪ*
4. በረዓድ ደስ ይበላችሁ – ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189፣ *ቃል ተተኳሪ*
5. ልጁን በማክበር ተቀበሉ ("መሳም") – ቢዲቢ 676፣ ኬቢ 730፣ *ፒይል ተተኳሪ*

**2፡12 "ልጁ"** በዚህ ትርጉም ላይ የሆነ ጥርጣሬ አለ። የዕብራይስጡ ቃል "ልጅ" בן (ቢዲቢ 61)፣ ቁ. 7 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ነገር ግን እዚህጋ בר ነው (ቢዲቢ 135፣ ማለትም፣ አራምኛ ቃል ለ"ልጅ፣" ምሳ. 31:2 [ሦስቴ])፣ እሱም በዕብራይስጥ ፍችው "ንጹሕ" ሊሆን የሚችል (ቢዲቢ 141 II፣ መዝ. 24:4፤ 73:1፤ ኢዮብ 11:4፤ ምሳ. 14:4)። አየተመት እና አኢመቅ ቁ. 11ሀ-12ሀ የሚተረጉሙት "በመንቀጥቀጥ እግሩን ሳሙ" በሚል ነው። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 164) "ልጁን በማክበር ተቀበሉ" የሚል ይሰጣል፣ "ለ" ደረጃ፣ (ማለትም፣ መጠነኛ ጥርጣሬ)።

አንዳንድ ሊቃውንት የሚገምቱት ቁ. 11-12 የሚያመለክቱት የአካባቢውን የጣዖት አምላኪ ሕዝቦችን እስከሆነ ድረስ፣ ሆን ተብሎ የተደረገ ዝውውር ተደርጓል፣ ከዕብራይስጡ "ልጅ" ወደ "አራምኛው "ልጅ።" አጠቃላዩ "የመገዛት" ግፊት ግልጽ ነው፣ ምንም እንኳ ቋንቋዊ ዝርዝሮች ባይሆኑም!

◘ **"እናንተም በመንገድ እንዳትጠፉ፥"** አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ሁለቱም ቃላት "መጥፋት" (ቢዲቢ 1፣ ኬቢ 2) እና "መንገድ" (ቢዲቢ 202) በኢጋጣሚ መዝሙር 1 ላይ ጥቅም ላይ በመዋላቸው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የየቀኑ ግንኙነት ነው፣ ከያህዌ እና ከመሢሑ ጋር። ኢየሱስ በርግጥ መዝሙር 1 እና 2ን ተጠቅሟል፣ ለማቴዎስ 5-7 የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር፣ በተለይም 7፡13፣21-23፣26-27።

◘ **"በእርሱ የታመኑ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው።"** የመዝሙር 2 የመጨረሻ ስንኝ ከመዝሙር 1 የመጀመሪያ ስንኝ ጋር ግንኙነት አለው፣ ጽሑፋዊ ዘዴ ኢንክሉሲኦ የሚባለው ይሆናል። እንዲያም፣ መዝሙር 1 - መዝሙር 2 የአንድ ጽሑፋዊ ምድብ ሥሪት አላቸው (ሐዋ. 13፡33)። ታልሙድ የሚለው መዝሙር 1 እና መዝሙር 2 አንድ መዝሙር ይመሠርታሉ (ቢ. ቤር. 9ለ-10ሀ)። እውነተኛ አማኝ ያህዌን የሚፈራ እና መገለጡን የሚያከብር ብፁዕ ነው! እምነትና ታማኝነት አንድጋ መኳዝ ይኖርባቸዋል። መጽደቅ እና መቀደስ ሊነጣጥሉ አይችልም!

ሁለቱም መዝ. 1፡1 እና 2፡12 አጽንዖት የሚሰጡት ለሰዎች ምርጫና ድርጊቶች ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የሕይወት ዘመን የእምነትና የመታዘዝ ጉዞ ነው።

ያህዌ በበርካታ ዘይቤዎች ተገልጿል፣ እንደ ደኅንነት ስፍራ፣ ዋስትና፣ እና ዕረፍት። እኛ ልንታመን/ ልንጠጋ እንችላለን

1. ዐለት – ዘዳ. 32:37፤ 2 ሳሙ. 22:2፣3፤ መዝ. 18:2
2. ምሽግ – 2 ሳሙ. 22:2፤ መዝ. 144:2
3. መሸሸጊያ – መዝ. 18:2፤ 62:2፤ 144:2
4. አዳኝ – 2 ሳሙ. 22:2፤ መዝ. 144:2
5. ጋሻ – ዘፍ. 15:1፤ 2 ሳሙ. 22:3፤ መዝ. 3:3፤ 18:2፤ 144:2፤ ምሳ. 30:5
6. የመዳን ቀንድ – 2 ሳሙ. 22:26፤ መዝ. 18:2፤ 75:10
7. እናቲት ወፍ – መዝ. 17:8፤ 36:7 (ደግሞም ዘዳ. 32:10-11)፤ 57:1፤ 63:7፤ 91:4 ማስታወሻ ተመልከት

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መኳዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር እንደ መሢሐዊ ለምን ተወሰደ?
2. አሕዛቡ አካባቢያዊ ናቸው ወይስ ዓለምን ሁሉ ያካተቱ?
3. "የተቀባ" የሚለውን አብራራ፣ ቁጥር 2 ላይ።
4. "የእሱ የተቀባው" እና ልጅ አንድ ናቸውን?
5. ይህ ኢየሱስን የሚያመለክት ከሆነ፣ ቁጥር 7 የሚያሳየው እንደ ተፈጠረ ነውን?

# መዝሙር 3
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የማለዳ ጸሎት አምላክን በመታመን | እግዚአብሔር የተቸገረ ሕዝቡን ይረዳል | ከግል ጠላት ለመታደግ የሚደረግ ጸሎት (ሰቆቃ) | የማለዳ ጸሎት ለዕርዳታ | የማለዳ የጻድቅ ጸሎት በመከራ ጊዜ |
| <u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>“የዳዊት መዝሙር፣ ከልጁ ከአቤሰሎም በሸሸ ጊዜ” (2ሳሙኤል 15-16) | | | | |
| 3:1-2 | | | | |
| 3:3-6 | | | | |
| | 3:1-2 | 3:1-2 | 3:1-2 | 3:1-2 |
| 3:7-8 | 3:3-4 | 3:3-4 | 3:3-4 | 3:3-4 |
| | 3:5-6 | 3:5-6 | 3:5-6 | 3:5-6 |
| | 3:7-8 | 3:7 | 3:7-8 | 3:7-8 |
| | | 3:8 | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 3፡1-2**
**1አቤቱ፥ የሚያስጨንቁኝ ምንኛ በዙ!**
**በኔ ላይ የሚቆሙት ብዙ ናቸው።**
**2ብዙ ሰዎች ነፍሴን፦**
**አምላከሽ አያድንሽም አልዋት።**

**3፡1-2** መዝሙረኛው የተጠመደ/በጠላቶቹ የተከበበ ይመስላል (ቢዲቢ 865 III)።

1. እየጨመሩ ሄደዋል (ዝኪ. ቁ. 6)
2. እያሻቀቡ ነው
3. እየተናገሩ ነው

“ብዙ” የሚለውን ሦስትዮሽ አጠቃቀም ተገንዘብ (ቢዲቢ 912I)። ለጻድቅ እግዚአብሔርን ለሚፈራ እንኳ ችግሮች አሉበት (ርግጠኛና ምናባዊ) በዚህ በወደቀ ዓለም። መዝሙራቱ ለአንባቢው የእምነትን ርዕዮተ-ዓለም ሊሰጡ ነው የሚሞክሩት (ማለትም፣ የእምነት ዓይን፣ 2 ነገ. 6፡17)። የመዝሙሩ ማስታወሻ የሚገልጸው የያህዌን መገኘትና ክብካቤ ነው!

አንዱ ሊደነቅ ይችላል እነዚህ ሰቆቃዎች እንዴት እንደሚሠሩ

1. በእኛ ጊዜ
2. በእኛ የእምነት ቡድኖች

ከእኛ ጋር የማይስማሙት የእግዚአብሔር ጠላት ናቸውን? እኔ የማስበው መዝሙራትን የተሻለ አጠቃቀም ለእምነት እንደ ማበረታቻ ቃል/በእግዚአብሔር መታመን እንጂ ከእኛ ጋር ለማይስማሙት ለማጥቂያ መሆን የለበትም! እውነተኞቹ ጠላቶች አምላካችንንና የእርሱን ክርስቶስ ያልተቀበሉት ናቸው!

**3፡2 "ነፍሴ"** *ይህ የዕብራይስጥ ቃል ኔፈሽ ነው* (ቢዲቢ 659፣ ኬቢ 711-713)፣ እሱም የሚገልጸው ዓየር የሚተነፍስ እንሰሳ ነው (ማለትም፣ ከዕብራይስጡ ቃል ትንፋሽና መንፈስ ጋር የሚዛመድ)። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው ለሰው ልጅ (ዘፍ. 2፡7) እና ለእንሰሳት (ዘፍ. 1፡24፤ 2፡19)።

ሰዎች ሁለቱንም ናቸው የዚህ ፍጥረት አካል እና በፈጣሪ መልክና አምሳል የተፈጠሩ (ዘፍ. 1፡26-27)። እኛ ሁለቱም አለን፣ ሥጋዊ ይዘትና መንፈሳዊ ይዘት።

▣ **"ሴላህ"** ይህ ቃል በጎዳጉ ላይ መሆኑን ተገንዘብ፣ ባጠቃላይም ለመዘምራን አለቃ፣ መዝ. 3፡2፣4፣8። ሥሩ ርግጠኝነት የለውም። እዚህጋ አንዳንድ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ ፡፡

1. ከፋርስ ሥር ለ "መዝሙር"
2. ከዕብራይስጥ סלל (ቢዲቢ 699) "ማንሣት፣" ማለትም፣ ከፍተኛ የድምጽ ቃና
3. ከዕብራይስጥ נצח (ቢዲቢ 663) ፍችው "ዘወትር፣" የሚያገለግለው እንደ "አሜን" ነው
4. ከLXX የሚገልጸው የሙዚቃ መሣርያዎችን ጣልቃ መግባት ነው

በእነዚህ ሁሉ ንድፈ-ሐሳቦች ግልጽ የሆነው ነገር ዘመናዊዎች በመዝሙረኛው ምን እንደሚያመለክት አለማወቃቸው ነው። እሱም በሔምቲ 70 ጊዜ እና በLXX ከ90 ጊዜ በላይ ጥቅም ላይ መዋሉ ነው። የመዝሙር መግቢያ VIII ተመልከት።

***መዝሙር ፡ 3፡3-6***

**3 አንተ ግን አቤቱ፥ መጠጊያዬ ነህ፥**
**ክብሬንና ራሴንም ከፍ ከፍ የምታደርገው አንተ ነህ።**
**4 በቃሌ ወደ እግዚአብሔር እጮሃለሁ**
**ከተቀደሰ ተራራውም ይሰማኛል። ሴላህ**
**5 እኔ ተኛሁ አንቀላፋሁም**
**እግዚአብሔርም ደግፎኛልና ነቃሁ።**
**6 ከሚከብቡኝ ከአእላፍ ሕዝብ አልፈራም።**

**3፡3-6 "ጌታ ሆይ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፣ መዝ. 1፡1 ላይ።

▣ **"አንተ... ነህ"** መዝሙረኛው በኃይለኛ ምናብ የያህዌን ማንነትና ሥራ ይገልጻል፣ ለአማኝ።

1. ጋሻ፣ ቁ. 3 – ዘፍ. 15:1፤ ዘዳ. 33:29፤ 2 ሳሙ. 22:3፤ መዝ. 28:7፤ 33:20፤ 59:11፤ 84:11፤ 115:9፣10፣11፤ 119:114፤ 144:2 (ደግሞም 1 ጴጥ. 1:5 ተመልከት)
2. ክብሬ፣ ቁ. 3 – መዝ. 62:7
   ሀ. ክብር
   ለ. ድል (ዝከ. አእት)
3. ራሴን ቀና የሚያደርገኝ፣ ቁ. 3
   ሀ. ድል በውጊያ ላይ
   ለ. በፍርድ ቤት በዳኛው እውቅና ማግኘት
   ሐ. ከሞት መዳን
4. ጸሎቴን መልሶልኛል፣ ቁ. 4
5. ይደግፈኛል፣ ቁ. 5
6. እንዳልፈራ ያደርገኛል፣ ቁ. 6

**3፡4 "ወደ እግዚአብሔር ጮኹኩ"** ይህ የዕርዳታ ጸሎት መዝ. 3፡7ሀ ሊሆን ይችላል። "ሰማኝም" የሚለው ውጤት፣ 3፡7ለ-8 ላይ ይታያል።

▣ **"ከተቀደሰ ተራራው"** ይህ የሚያመለክተው መቅደስ ነው፣ በብኪ ምናብ፣ ያህዌ በኪሩቤል ክንፎች መካከል በኪዳኑ ታቦት ላይ የሚኖርበት። ይህም ሰማይና ምድር (መንፈሳዊው እና ሥጋዊው) የሚጋጠሙበት ስፍራ ነው!

**3፡5** *መተኛት ይቻላል፣ ከያህዌ መገኘት የተነሣ፣ ሰላም፣ እና መጠበቅ* (*መዝ*. 4፡8፤ *ምሳ*. 3፡24)። *መዝሙር* 3፡5*ሀ ዕረፍት ላለው የምሽት እንቅልፍ ፈሊጥ*! *ይህም ይቻላል፣ አንዱ በያህዌ ላይ ባለው እምነትና መታመን፣ በእሱ መገኘት፣ በእሱ ተስፋዎች፣ በእርሱ ባሕርይ*!

**3፡6** *ይህ ግነታዊ፣ ፈሊጣዊ ቋንቋ ነው*። "*እእላፍ*" *የሚለው ቃል* (ቢ.ዲ.ቢ. 914) *ሊቆጠር ለማይችል ሠራዊት ፈሊጥ ነው*። *የብዙ ቁጥሩ* (*እንደዚሁ*) *ይህንኑ ያጠናክራል* (*ዘዳ*. 33፡2፣17፤ 1 *ሳሙ*. 18:7፤ *ሚክያስ* 6:7)።

***መዝሙር ፡ 3፡7-8***

***[7]ተነሥ፥ አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ አድነኝ***
***አንተ የጠላቶቼን መንጋጋ መትተሃልና፥***
***የክፉዎችንም ጥርስ ሰብረሃልና።***
***[8]ማዳን የእግዚአብሔር ነው፥***
***በረከትህም በሕዝብህ ላይ ነው! ሴላህ***

**3:7** *ይህ ቁጥር የሚጀምረው በሁለት ተተኳሪዎች ነው* (*ማለትም፣ የጸሎት ጥያቄዎች*)።

1. *ተነሥ* – ቢ.ዲ.ቢ. 877፣ ኬቢ. 1086፣ *ቃል ተተኳሪ፣ ያህዌ እንዲሠራ አጥብቆ መጠየቅ በሚል መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ዘኁ*. 10:35፤ *መዝ*. 7:6፤ 9:19፤ 10:12፤ 44:26፤ 68:1፤ 74:22፤ 82:8፤ 132:8፤ *ጠላት እንደ* "*ተነሣ፣*" *አሁን ደግሞ ያህዌ እንዲነሣ ዘማሪው ጥሪ ያቀርባል* (*ማለትም፣ ከዙፋኑ ላይ*)!
2. *አድን* – ቢ.ዲ.ቢ. 446፣ ኬቢ. 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ፣ እሱም በብኪ የሚገልጸው ከፈተና፣ ከሥቃይ፣ ከዚህ ዓለም ጉዳዮች መታደግን ነው* (*መዝ*. 3:8)

**ልዩ ርዕስ፡ ድኅነት (*መዳን*)**

*ይህ ቃል* (ቢ.ዲ.ቢ. 447) *በርካታ ፍችዎች አሉት*።

1. *ደኅንነት፣ ብልጽግና፣ ኢዮብ* 30፡15
2. *መለኮታዊ ድኅነት እሱም በሥጋዊም ሆነ በመንፈሳዊ ገጽታ ዙሪያ የሚዞር*
   *ሀ*. *ዘፍ*. 49፡18
   *ለ*. *ዘዳ*. 32፡15*ሐ*. *መዝ*. 3፡2፣8፤ 22:1፤ 35:3፤ 62:2፤ 69:29፤ 70:5፤ 78:22፤ 80:3፤ 89:26፤ 91:16፤ 106:4፤ 140:7
   *መ*. *ኢሳ*. 12:2፤ 33:2፤ 51:6፣8፤ 52:7፣10፤ 56:1፤ 59:11፤ 60:18፤ 62:1
3. *የሥጋዊና መንፈሳዊ መዳን ደኅንነት በዮናስ* 2፡9-10 *ላይ በግልጽ ተቀምጧል*
4. "*ተደሰቱ*" *የሚለው ዘወትር የሚዛመደው ከያህዌ ማዳን ጋር ነው፣* 1*ኛ ሳሙ*. 2፡1፤ *ኢሳ*. 25:9፤ 26:1፤ *መዝ*. 9:14፤ 13:5፤ 35:9

*ደኅንነት የያህዌን ዋነኛ ሐሳብ የሆነውን ኅብረትና ማኅበረሰብ እሱ ከፈጠረው ሰው ጋር ተግባራዊ መሆኑን ማካተቱ ነው*። *እሱም ግለሰባዊና ማኅበረሰባዊ ሙሉነትን ያካትታል*!

▣ ***"መትተሃልና... ሰብረሃልና"*** *ያህዌ መታደግን በኃይል ያመጣል፣ በመዝሙረኛው ጠላቶች ላይ*።

1. *መትተሃልና* – ቢ.ዲ.ቢ. 645፣ ኬቢ. 697፣ *ሂፊል የተጠናቀቀ*
2. *ሰብረሃልና* – ቢ.ዲ.ቢ. 990፣ ኬቢ. 1402፣ *ፒይል የተጠናቀቀ*

"*አገጭ*" (ቢ.ዲ.ቢ. 534 I) *እና* "*ጥርስ*" 9ቢ.ዲ.ቢ. 1042 I) *የዕፍረትና የመሸነፍ ፈሊጦች ናቸው* (1 *ነገ*. 22:24፤ *ኢዮብ* 16:10፤ *መዝ*. 58:6፤ *ሚኪያስ* 5:1)። *እሱም በተለይ የሚጠቅሰው የጥላቻ ቃላቸውን ነው* (*ዝኪ. ቁ*. 2)።

**3፡8** *ምንም ግሦች የሉም፣ መዝ*. 3፡8 *ላይ*። *ዘወትር መጽሐፍ ቅዱሳዊው ዕብራይስጥ* "*የመሆን*" *ግሥ በአንባቢው የተጨመረ ነው*።

▣ **"ሴላህ"** *መዝ*. 3፡2 *ላይ ማስታወሻ ተመልከት*።

**3፡9** *የአንድ ግለሰብ ሰቆቃ የአጠቃላዩን ሁኔታ ለማንጸባረቅ እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋለ ተገንዘብ* (*ማለትም፣* "*ሕዝብህ፣*" *የቁ*. 9፤ *መዝ*. 25፡22፤ 28፡9)። *ያህዌ ደኅንነትን/መታደግን የሚያመጣው ለሚጠይቁ ግለሰቦች ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ለሚጠይቁ ሕዝቦችም እንጂ ነው* (*ማለትም፣* 2 *ዜና*. 7፡14)።

## የውይይት ጥያቄዎች

*ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡*

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ጠላቶች እነማን ናቸው?
2. እነርሱ የያህዌን ማዳን ለምን ካዱ?
3. “ተነሥ” የሚለው ተተኳሪ ምን ማለት ነው?
   የእሱስ ታሳቢ ዳራዎች ምንድናቸው?
4. “ሴላህ” ምን ማለት ነው?

## መዝሙር 4
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የምሽት ጸሎት በአምላክ ስለመታመን<br>ኤምቲ መግቢያ<br>"ለመዘምራን ዓለቃ፣ በበገናዎች የዳዊት መዝሙር<br>4:1 | የታማኝ ደኅንነት | ከግል ጠላት ለመታደግ ጸሎት (ሰቆቃ) | የምሽት ጸሎት ለዕርዳታ | የምሽት ጸሎት |
| 4:2-3 | 4:1 | 4:1 | 4:1 | 4:1 |
| | 4:2-3 | 4:2 | 4:2 | 4:2 |
| 4:4-5 | | 4:3 | 4:3 | 4:3 |
| | 4:4-5 | 4:4-5 | 4:4-5 | 4:4 |
| 4:6-8 | | | | 4:5 |
| | 4:6-8 | 4:6-7 | 4:6-7 | 4:6 |
| | | | | 4:7 |
| | | 4:8 | 4:8 | 4:8 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር

ሀ. የመከፈቻ ጸሎት ለእግዚአብሔር፣ ቁ.1

ለ. ለጠላቶች የሚያመለክት፣ ቁ. 2-3

ሐ. ከእግዚአብሔር ተገቢ ምላሽ የሚጠይቅ፣ ቁ. 4-5

መ. የመዝጊያ ጸሎት ለእግዚአብሔር፣ ቁ. 6-8

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 4:1**
**1የጽድቄ አምላክ በጠራሁት ጊዜ መለሰልኝ፥**
**በጭንቀቴም አሰፋህልኝ ማረኝ፥**
**ጸሎቴንም ስማ።**

**4:1** እግዚአብሔርን ለመለመን ጥቅም ላይ የዋሉትን ተተኳሪዎች አስተውል።

1. *መለሰለኝ* – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 27:7
2. ለእኔም በጸጋው ሆነልኝ – ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 25:16፤ 69:16
3. ጸሎቴን ሰማ – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 17:6፤ 39:12

መዝሙረኛው እግዚአብሔር እንደሚያደምጠውና እንደሚሠራ ተስፋ አድርጓል (መዝ. 3:4፤ 6:8፣9፤ 17:6፤ 86:7)! ጸሎት ጥያቄ ብቻ አይደለም፣ እሱ ኅብረትም ነው! እሱን እንሻዋለን፣ ከተመለሱ ጥያቄዎቻችን ይልቅ!

▣ መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ባሕርይ እንዴት እንደገለጸ ተገንዘብ።

1. ጽድቄ እግዚአብሔር ሆይ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:5 ላይ)
2. ከመከራ የሚያወጣኝ እግዚአብሔር ሆይ

በርካታ ተውላጠ ስሞች በእነዚህ ቀዳሚ ሁለት ቁጥሮች ላይ ይገኛሉ! ያህዌ ብቸኛው "የጽድቅ" ምንጭ ነው፣ ሰላምን የሚያመጣ (በሁለቱም፣ በሥጋዊ እና በመንፈሳዊ)!

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ያሰፋልኛል"** |
| **አየተመት፣ LXX** | **"ስፍራ ይሰጠኛል"** |
| **አኢመቅ** | **"በስፋት ያኖረኛል"** |
| **ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ** | **"ነጻ ያወጣኛል"** |

የዕብራይስጡ ቃል (ቢዲቢ 931፣ ኬቢ 1210፣ *ሂፊል የተጠናቀቀ*) ሰፋ ላለ ቦታ ፈሊጥ ነው (መዝ. 18:19)፣ "የክልከላ" ተቃራኒ (ማለትም፣ ጭቆና፣ መከራ፣ ጠባብ መንገዶች፣ ቢዲቢ 865፣ "ጭንቀት")። የእርሱ ዘይቤአዊ ባሕርይ ሊታይ ይችላል፣ ዘፍ. 26:22፤ ዘዳ. 33:20፤ መዝ. 25:17፤ ኢሳ. 54:2፤ 57:8 ላይ።

**መዝሙር ፡ 4፡2-3**

**[2]እናንት የሰው ልጆች፥ እስከ መቼ ድረስ ልባችሁን ታከብዳላችሁ?**
**[3]እግዚአብሔር በጻድቁ እንደ ተገለጠ እወቁ**
**እግዚአብሔር ወደ እርሱ በተጣራሁ ጊዜ ይሰማኛል።**

**4፡2** ደራሲው ተጻራሪ መቼቶችን የሚያዳብረው በሁለት ጥያቄዎች ነው፣ በሚቃወሙት ላይ የሚያተኩር።

1. መሳለቅ/ማሳፈር – ቢዲቢ 484
2. ከንቱነት/ከንቱ ቃላት – ቢዲቢ 938
3. ማሳት/ውሸት – ቢዲቢ 469

እግዚአብሔር "ጽድቄ" ተብሎ እንደተጠራ፣ መዝ. 4:1 ላይ፣ አሁንም የመዝሙረኛውን ጉዳት የሚያደርጉትን አዝማሚያቸውን፣ ሐሳባቸውን፣ እና ድርጊታቸውን እንደሚገልጽ ተጠርቷል።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ክብሬ መሳለቂያ ሆነ"** |
| **አኪጀት** | **"ክብሬ ማፈሪያ ሆነ"** |
| **አኢመቅ** | **"ልቤ ከብዶኛል"** |

አኢመቅ LXXን ይከተላል፣ እሱም ባጠቃላይ ከተለየ የዕብራይስጥ ጽሑፍ የተረጎመ፣ ከኤምቲ ይልቅ። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 165) ለኤምቲ "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል (ምክንያታዊ ጥርጣሬ)።

▣ **"ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝሙር 3፡2 ላይ።

**4፡3** ጠላቶቹ ለመዝሙረኛው ጥያቄዎች እንዴት መልስ ሰጡ፣ ቁ. 2?

1. ጌታ መመደቡን ያውቃሉ (ተተኳሪ) (LXX፣ "ለቅዱሱ አስደናቂ ነገሮችን ያደርጋል" አኢመቅ፣ አእመቅ) ለራሱ መልካም ሰው (ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት የሚሰጠን ደረጃ "ሀ" ነው [እጅግ ከፍ ያለ ሁኔታ])
2. እግዚአብሔር መልካምን ሰው ይሰማል (ቢዲቢ 339) ሲጸልይ

ያህዌ እውነተኛ አማኞቹን ያውቃል፣ ምላሽም ይሰጣል። እነርሱን ማጥቃት እሱን ማጥቃት ነው!

**መዝሙር ፡ 4፡4-5**

**[4]ተቈጡ፥ ነገር ግን ኃጢአትን አታድርጉ**
**በመኝታችሁ ሳላችሁ በልባችሁ አስቡ ዝም በሉ።** **ሴላህ።**
**[5]የጽድቅን መሥዋዕት ሠዉ፥**
**በእግዚአብሔርም ታመኑ።**

**4፡4-5** ተለጣጣቂ ትእዛዛት ይገኛሉ፣ መዝሙረኛው የሚሰነዝረው፣ ጠላቱ እንዴት መሆን እንዳለበት (ማለትም፣ "የሰው ልጆች ሆይ፣" ቁ. 2)።

1. ተንቀጥቀጡ – ቢዲቢ 919፣ ኬቢ 1182፣ *ተተኳሪ*
2. ኃጢአትን አታድርጉ – ቢዲቢ 306፣ ኬቢ 305፣ የተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. በልባችሁ አስቡ (ተናገሩ) – ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ ተተኳሪ፣ መዝ. 77:6
4. ዝም በሉ – ቢዲቢ 198፣ ኬቢ 226፣ ተተኳሪ
5. *መሥዋዕት ሠዉ* – ቢዲቢ 256፣ ኬቢ 261፣ ተተኳሪ
6. በእግዚአብሔር *ታመኑ* – ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ ተተኳሪ፣ መዝ. 37:3፤ 62:8

**4፡4** ከላይ ያለው ቁጥር ሁለት በጳውሎስ ተጠቅሷል፣ ኤፌ. 4፡26 ላይ፣ ከዘዳ. 24፡15 ጋር ተደባልቆ፣ "ተቆጡ፣ ኃጢአትንም አታድርጉ፣" እሱም ከLXX የሆነ። ኤምቲ "ተንቀጥቀጡ" የሚል አለው፣ እሱም "ፍርሃትን" የሚጠቅስ (ኢሳ. 32፡11፤ ሚክያስ 7፡17፤ ዕን. 3፡16)፣ ቁጣን ሳይሆን።

▣ **"ዝም በሉ"** *ቃሉ* (ቢዲቢ 198፣ ኬቢ 226) በርካታ አጠቃቀሞች አሉት።

1. በውጊያ ፍርሃት – ዘጸ. 15:14-16
2. በፍርድ ዝም ማለት – 2 ሳሙ. 2:9
3. በሞት ዝም ማለት – መዝ. 31:17፤ 94:17፤ ኤር. 48:2፤ 49:26
4. በጥፋት መደንገጥ፣ ዝም ማለት – ኤር. 25:37
5. የጥበብ ዝምታ በተገቢው ጊዜ – መዝ. 4:4፤ 62:5፤ 131:2፤ አሞጽ 5:13

▣ **"ሴላህ"** *መዝሙር 3፡2 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።*

**4፡5 "በጌታ *ታመኑ*"** ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120)።

1. ለኃጢአተኞች ጥሪ — መዝ. 4፡5
2. ለታማኞች ጥሪ — መዝ. 9:10፤ 32:10፤ 37:3፣5፤ 40:3፤ 55:23፤ 56:4፣11፤ 84:12፤ 91:2፤ 112:7፤ 115:11፤ 125:1፤ 143:8፤ ምሳ. 16:20፤ 29:25፤ ኢሳ. 26:3-4
3. ንጉሥ – መዝ. 21:7፤ 25:2፤ 26:1፤ 28:7
4. አባቶች – መዝ. 22:4-5
5. ሕዝቦች ሆይ – መዝ. 62:8፤ 115:9
6. ካህናት – መዝ. 115:10

በያህዌ እና በቃሉ ማመን ነው፣ ተስፋን የሚያመጣ (ዝከ. ቁ. 3)፣ ደስታ (ዝከ. ቁ. 7)፣ እና ሰላም (ዝከ. ቁ. 8) በዚህ በወደቀ ዓለም።

***መዝሙር ፡ 4፡6-8***

**6 በጎውን ማን ያሳየናል? የሚሉ ብዙ ናቸው።**
**አቤቱ፥ የፊትህ ብርሃን በላያችን ታወቀ።**
**7 በልቤ ደስታን ጨመርህ**
**ከስንዴ ፍሬና ከወይን ከዘይትም ይልቅ በዛ።**
**8 በሰላም እተኛለሁ አንቀላፋለሁም**
**አቤቱ፥ አንተ ብቻህን በእምነት አሳድረኸኛልና።**

**4፡6-7** እንደ ቁጥር 2፣ ቁጥር 6 በጥያቄ ይጀምራል፣ እሱም የመዝሙረኛውን ጠላቶች አዝማሚያን፣ የውስጥ ሐሳብን፣ እና ድርጊትን የሚያንጸባርቅ።

መልሱ ጥያቄው ነው (ተተኳሪ)፣ ያህዌ "የፊትህ ብርሃን በላያችን ታወቀ" (ዘኍ. 6:26፤ መዝ. 80:3፣7፣19)። ይህ የመለኮት ፊሊጥ ነው፣ ለታማኝ (ቁ. 5ለ) አገልጋዮቹ ግላዊ እይታ እንደሚወስድና ምሕረቱን እንደሚያበዛ (መዝ. 27፡1፤ ሚክያስ 7፡8)። ያህዌ

1. በዘማሪው ልብ ደስታን ያስቀምጣል
2. በዘማሪው ልብ ሰላምን ያስቀምጣል
3. በዘማሪው ልብ ደኅንነትን ያስቀምጣል

ዘኍ. 6፡26 ላይ "ያነሣል" የሚለው ግሥ נשׂא ነው፣ ቢዲቢ 669፣ እዚህ ግን እሱ נסה ነው (ኬቢ 702)። ባጠቃላይ እነርሱ የአንድ ሥር ሁለት መልኮች ናቸው (ዝከ. ቢዲቢ 650፣ ኬቢ 702፣ አእመቅ፣ ገጽ 853፣ ቁ. 6)።

**4፡7 "ልብ"** ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡- ልብ

1. “ካርዲያ” *Kardia* የሚለው የግሪኩ ቃል leb ልብ የሚለው የእብራይስጡን ቃል (BDB 523) ለማንጸባረቅ በሰብትዋጅንት እና በአዲስ ኪዳን ውስጥ ተጠቅሷል፡፡ ይህ ቃል በተለያዩ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል (ባውር፣አሪንድት፣ ጊንግሪች፣ እና ዳንከር፤ *A Greek-English Lexicon,* ገጽ. 403-404) ፡፡ የተፈጥሮአዊ ሕይወት ማእከል፤ ለሰው የሚደረግ ተለዋዋጭ ዘይቤ (የሐዋ.14:17፤ 2ኛ ቆሮ.3:2-3፤ ያዕ. 5:5)
2. የመንፈሳዊ ሕይወት ማዕከል (ማለትም ሞራላዊ)
   ሀ. እግዚአብሔር ልብን ያውቃል (ሉቃ.16:15፤ሮሜ 8:27፤ 1ኛ ቆሮ. 14:25፤ 1ኛ ተሰሎ.2:4፤ ራዕ.2:23)
   ለ. የሰውን ልጅ መንፈሳዊ ሕይወት የሚያመለክት (ማቴ.15:18-19፤ ሮሜ. 6:17፤ 1ኛ ጢሞ. 1:5፤ 2ኛ ጢሞ. 2:22፤ 1ኛ ጴጥ. 1:22)
3. የአስተሳሰብ ሕይወት ማዕከል (እውቀት ማቴ.13:15፤24:48፤ የሐዋ.7:23፤16:14፤28:27፤ሮሜ.1:21፤10:6፤2ኛ ቆሮ.4:6፤ኤፌ. 1:18፤4:18፤ ያዕ.1:26፤ 2ኛ ጴጥ.1:19፤ራእ.18:7፤ ልብ ከአእምሮ ገር ተመሳሳይ ነው በ2ኛ ቆሮ.3:14-15 እና ፊልጵ 4:7)
4. የፈቃድ ማዕከል (ማለትም ፈቃድ የሐዋ.5:4፤11:23፤1ኛ ቆሮ. 4:5፤5:37፤2ኛ ቆሮ.9:7)፡፡
5. የስሜቶቻችን ማዕከል (ማቴ.5:28፤ የሐዋ. 2:26፡37፤7:54፤21:13፤ሮሜ 1:24፤ 2ኛ ቆሮ. 2:4፤7:3፤ኤፌ.6:22፤ ፊልጵ.1:7)፡፡
6. የመንፈስ ቅዱስ እንቅስቃሴ ልዩ ሥፍራ (ሮሜ 5:5፤ 2ኛ ቆሮ. 1:22፤ገላ.4:6/ክርስቶስ በልባችን፡-ኤፌ. 3:17/)
7. ልብ የአንድን ሰው ሁለንተና የሚያመለክት ተለዋዋጭ ዘይቤ ነው (ዘይቤያዊ ቋንቋ) ነው (ማቴ.22:37 ከዘዳ. 6:5 የተወሰደ)፡፡ ሃሳቦች፣ ዓላማዎች፣ ድርጊቶች አንድ ላይ ተቀናጅተው የግለሰቡን ማንነት ያሳያሉ፡፡ ብሉይ ኪዳን ጎላ ያለ የቃሉ አጠቃቀም አለው፡፡
   ሀ. ዘፍ. 6:6፤8:21 “እግዚአብሔር በልቡ ተጸጸተ” ሆሴ. 11:8-9ንም አስታውል
   ለ. ዘዳ.4:29፤ 6:5 “በፍጹም ልብህና በፍጹም ነፍስህ”
   ሐ. ዘዳ. 10:16 “ያልተገረዘ ልብ” እና ሮሜ 2:29፡፡
   መ. ሕዝ.12:31-32 “አዲስ ልብ”
   ሠ. ሕዝ 36:26 “አዲስ ልብ” እና “የድንጋይ ልብ”

◘ **“አዲስ እህል”** የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 47) የሚጠቅሰው የዕብራይስጡ ኤምኤስኤስ፣ በሙት ባሕር ጥቅሎች የተገኘው፣ እንዲሁም LXX እና ቫልጌት “የወይራ ዘይት” ይጨምራሉ፣ ከ “እህል” በኋላ እና ከ “አዲስ ወይን” በፊት፣ እሱም ከዘዳግም 7:13፤ 11:14፤ 12:17፤ 14:23፤ 18:4፤ 28:51 የመጣ ሊሆን የሚችል።

◘ **“አዲስ ወይን”** ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አዝማሚያ በአልኮል እና በአልኮለኝነት

I. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃላት
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
   1. ያይን - ይህ የወይን አጠቃላይ ቃል ነው (ቢዲቢ 406)፣ እሱም 141 ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ።ሥርወ ቃሉ ርግጠኛ አይደለም፣ ምክንያቱም ከዕብራይስጥ ሥርወ ቃል ስላልሆነ። እሱም የሚሆነው የኮመጠጠ የፍራፍሬ ጭማቂ፣ ባብዛኛውም ወይን ነው። ጥቂት ሁነኛ ምንባቦች፣ ዘፍ. 9፡21፤ ዘጸ. 29፡40፤ ዘኁ. 15፡5፤10።
   2. ቲሮሽ - ይህ “ጉሽ የወይን ጠጅ” ነው (ቢዲቢ 440)። በቅርብ ምስራቅ የዓየር ሁኔታ ምክንያት፣ ኩምጠጣ የሚጀምረው ጭማቂው ከተሰናዳ ከስድስት ሰዓት በኋላ ነው። ይህ ቃል የሚያመለክተው በመኮምጠጥ ሂደት ላይ ላለ ወይን ነው። ለሁነኛ ምንባቦች፣ ዘዳ. 12፡17፤ 18፡4፤ ኢሳ. 62፡8-9፤ ሆሴ. 4፡11 ተመልከት።
   3. አሲስ - ይህ የአልኮል መጠጥ ነው፣ (“ጣፋጭ ወይን” ቢዲቢ 7799፤ ምሳ. ኢዩኤል 1፡5፤ ኢሳ. 49፡26)።
   4. ሴካር - ይህ “ጠንካራ መጠጥ” ነው (ቢዲቢ 1016)። የዕብራይስጡ ሥር ጥቅም ላይ የሚውለው “ሰካራም” ወይም “ሰካር” በሚል ነው። እሱም አንዳች የተጨመረበት ይኖራል የበለጠ አስካሪ እንዲሆን። እሱም ከያይን ጋር ትይዩ ነው (ምሳ. 20፡1፤ 31፡6፤ ኢሳ. 28፡7)።

   ለ. አዲስ ኪዳን
   1. ኦዪኖስ - ከግሪኩ ያይን ጋር አቻ ነው
   2. ኒኦስ ኦዪኖስ (ጉሽ ወይን) የግሪኩ አቻ ቲሮሽ (ማርቆስ 2፡22)
   3. ግሊዩኮስ ቪኖስ (ጣፋጭ ወይን፣ ኤሲስ) - በአዲስነት መፍላት ላይ ያለ ወይን (ሐዋ. 2፡13)

II. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አጠቃቀሙ
   ሀ. ብሉይ ኪዳን
   1. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው (ዘፍ. 27፡28፤ መዝ. 104፡14-15፤ መክ. 9፡7፤ ሆሴ. 2፡8-9፤ ኢዩ. 2፡19፤24፤ አሞጽ 9፡13፤ ዘካ. 10፡7)።
   2. ወይን የመሥዋዕታዊ ስጦታው አንደኛው አካል ነው (ዘጸ. 29፡40፤ ሌዋ. 23፡13፡ ዘኁ. 15፡7፤10፤ 28፡14፤ ዘዳ. 14፡26፤ መሳ 9፡13)።
   3. ወይን እንደ መድኃኒት ያገለግላል (2ኛ ሳሙ. 16፡2፤ ምሳ. 31፡6-7)።
   4. ወይን ተጨባጭ ችግር ሊሆን ይችላል (ኖህ - ዘፍ. 9፡21፤ ሎጥ- ዘፍ. 19፡33፤35፤ ሳምሶን- መሳ. 16፡19፤ ናባል- 1ኛ ሳሙ. 25፡36፤ ኦርዮ- 2ኛ ሳሙ. 11፡13፤ አምኖን- 2ኛ ሳሙ. 13፡28፤ ኢላህ- 1ኛ ነገሥ. 16፡9፤ ቤነሃዳድ- 1ኛ ነገሥ. 20፡12፤ ገዥዎች- አሞጽ 6፡6፤ እና ሴቶች- አሞጽ 4)።
   5. ወይን ሊያዛባ ይችላል (ምሳ. 20፡1፤ 23፡29-35፤ 31፡4-5፤ ኢሳ. 5፡11፤22፤ 19፡14፤ 28፡7-8፤ ሆሴዕ 4፡11)።
   6. ወይን ለተወሰኑ ወገኖች ክልክል ነው (ካህናት በሥራ ላይ፣ ሌዋ. 10፡9፤ ሕዝ. 44፡21፤ ናዝራውያን፤ ዘኁልቁ 6፤ እና ገዥዎች፣ ምሳ. 31፡4-5፤ ኢሳ.56፡11-12፤ ሆሴዕ 7፡5)።

7. ወይም እንደ የፍጻሜ መዳረሻነት መቼት ተደርጎ ተወስዷል፣ (አሞጽ 9፡13፤ አዩኤል 3፡18፤ ዘካ. 9፡17)።

ለ. ተረፈ መጽሐፍ ቅዱስ

1. ወይን በልኩ በጣም ይረዳል (መክብብ 31፡27-30)።
2. ራቢዎች የሚሉት፣ "ወይን ከመድኃኒት ሁሉ ታላቁ ነው፣ ወይን ሲያልቅ ነው ሌላ መድኃኒት የሚያስፈልገው።" (ባባ ባዝራ 58ለ)

ሐ. አዲስ ኪዳን

1. ኢየሱስ በርካታ ውኃ ወደ ወይን ቀይሯል (ዮሐንስ 2፡1-11)።
2. ኢየሱስ ወይን ጠጥቷል (ማቴ. 11፡18-19፤ ሉቃስ 7፡33-34፤ 22፡17)።
3. ጴጥሮስ በስካር ተከሷል፣ በጰንጠቆስጤ "ጉሽ ወይን"፣ (ሐዋ. 2፡13)።
4. ወይን እንደ መድኃኒት ያገለግላል (ማርቆስ15፡23፤ ሉቃስ 10፡34፤ 1ኛ ጢሞ. 5፡23)።
5. መሪዎች ጠጪ መሆን አይኖርባቸውም። ይህም ባጠቃላይ መጠጥን አለመቅመስ ማለት አይደለም (1ኛ ጢሞ. 3፡3፣8፤ ቲቶ 1፡7፤ 2፡3፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡3)።
6. ወይን መንፈሳዊ ለሆነ መቼት ያገለግላል (ማቴ. 22፡1፤ ራዕ. 19፡9)።
7. ጠጪነት የተወገዘ ነው (ማቴ. 24፡49፤ ሉቃስ 12፡45፤ 21፡34፤ 1ኛ ቆሮ. 5፡11-13፤ 6፡10፤ ገላ. 5፡21፤ 1ኛ ጴጥ. 4፡3፤ ሮሜ 13፡13-14)።

III. ሥነ መለኮታዊ ይዘት

ሀ. ተቃርኗዊ ክርክር

1. ወይን የእግዚአብሔር ስጦታ ነው።
2. ሰካራምነት ዋነኛው ችግር ነው።
3. አማኞች በአንዳንድ ባህሎች ነጻነታቸውን መገደብ ይኖርባቸዋል፣ ለወንጌል ብለው (ማቴ. 15፡1-20፤ ማርቆስ 7፡1-23፤ 1ኛ ቆሮንቶስ 8-10፤ ሮሜ 14)።

ለ. ከተወሰነው ገደብ በላይ የመውጣት ዝንባሌ

1. እግዚአብሔር የመልካም ነገር ሁሉ ምንጭ ነው።
2. የወደቀው የሰው ልጅ ሁሉንም የእግዚአብሔር ስጦታዎች እግዚአብሔር ካስቀመጠለት ገደብ በላይ በመውሰድ አበላሽቷቸዋል።

ሐ. ያላግባብ መጠቀሙ ከእኛ እንጂ ከነገሮች አይደለም። በሥጋዊ ተፈጥሮ ምንም ክፉ የለም (ማርቆስ 7፡18-23፤ ሮሜ 14፡14፣20፤ 1ኛ ቆሮ. 10፡25-26፤ 1ኛ ጢሞ. 4፡4፤ ቲቶ 1፡15)።

IV. የአንደኛው ክፍለ ዘመን የአይሁድ ባህልና አልኮል (ሆምጣጤ)

ሀ. መኮምጠጥ የሚጀምረው ወዲያው ነው፣ በግምት ከ6 ሰዓት በኋላ፣ ወይኑ ተረግጦ ሲያበቃ።

ለ. የአይሁድ ባህል እንደሚለው ከበስተላዩ ልከኛ አረፋ መታየት ሲጀምር (የመፍላት ምልክት)፣ የወይን መባ ለመስጠት ይደርሳል (ማ አሴሮዝ 1፡7)። እሱም "አዲስ ወይን" ወይም "ጣፋጭ ወይን" ይባላል።

ሐ. የመጀመሪያው አስካሪ ፍላት የሚያበቃው ከአንድ ሳምንት በኋላ ነው።

መ. ሁለተኛው ፍላት 40 ቀን ይወስዳል። በዚህ ጊዜ "ያረጀ ወይን" እንደ ሆነ ይቆጠራል፣ በመሠዊያው ላይም ለመሥዋዕትነት ይቀርባል (ኢድሁዮዝ 6፡1)።

ሠ. ሰፈፉ ላይ የረጋ ወይን (ያረጀ ወይን) መልካን እንደሆነ ይቆጠራል፣ ነገር ግን ጥቅም ላይ ከመዋሉ በፊት መከለስ አለበት።

ረ. ወይን በተገቢው አረጀ የሚባለው ከፍላት ከአንድ ዓመት በኋላ ነው። ሦስት ዓመት ትልቁ ጊዜ ነው፣ ወይንን በተገቢው ለማስቀመጥ። እሱም "ያረጀ ወይን" ይባላል፣ ስለሆነም በውሀ መበረዝ ይኖርበታል።

ሰ. ባለፉት 100 ዓመታት በንጹሕ ቦታ እና ቅመም በመጨመር ኮምጣጥነቱን ማሻሻል ተችሏል። የጥንቱ ዓለም የኩምጠጣን ተፈጥሯዊ ሂደት ሊያስቀረው አልቻለም።

V. የመዝጊያ መግለጫ

ሀ. ያንተ ልምድ፣ ሥነ መለኮት፣ እና የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ የኢየሱስንና የአንደኛውን ክፍለ ዘመን አይሁድ/ወይም ክርስቲያናዊ ባህል እንዳያንኳስስ ተጠንቀቅ! እነሱ ጨርሰው አልኮል የማይቀምሱ አልነበሩም።

ለ. እኔ የአልኮል ማህበራዊ ጠቀሜታ ተከራካሪ አይደለሁም። ሆኖም፣ ብዙዎች በዚህ ጉዳይ ላይ የመጽሐፍ ቅዱስን አቋም ስለሚያጋንኑ እናም አሁን ልዕለ ጽድቅ የተመሠረተው በባህል/በመሠረተ እምነት ላይ ባለ አድሏዊነት በመሆኑ።

ሐ. ለእኔ፣ ሮሜ 14 እና 1ኛ ቆሮ. 8-10 በፍቅርና በአክብሮት ላይ የተመሠረተ ይዘትና መመሪያ ይሰጡኛል፣ ይህም ለአማኞችና ለወንጌል ስርጭት በሁሉም ባህል፣ ግለሰባዊ ነጻነት ወይም ፍርዳዊ ሂስ ሳይሆን። መጽሐፍ ቅዱስ ብቻውን የእምነትና የተግባር ምንጭ ከሆነ፣ እናም ሁላችንም ይሄንን ጉዳይ ዳግም ልናጤነው ይገባል።

መ. ጨርሶ መታቀብን እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ ብንወስደው፣ ስለ ኢየሱስ ምን እንላለን፣ እንዲሁም ስለ ዘመናዊዎቹ ባህሎች፣ በመደበኛነት ወይንን የሚጠቀሙ፣ (ለምሳሌ፣ አውሮጳ፣ እስራኤል፣ አርጀንቲና)?

**4፡8**
**አአመመቅ፣ አኪጆት**
**አየተመት፣ የተእት፣**

**አኢመቅ** **"አቤቱ ጌታ ሆይ፥ አንተ ብቻህን በደኅንነት አሳድረኸኛልና።"**

**አእት፣ ጀፒኤስአኤ** (ግርጌ ማስታወሻ) **"አቤቱ ጌታ ሆይ፥ አንተ ብቻህን፣ በደኅንነት አሳድረኸኛልና።"**

"ብቻ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 94) ሊያጠናክር የሚችለው

1. ጌታን
2. ታማኝ ተከታይ፣ እሱም ብቻውን የሚተኛ (ማለትም፣ ምንም ጠላቶች የሉም)

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "የሰው ልጆች" እነማናቸው? እንዴት ነው ባሕርያቸው የተሳለው?
2. የዕብራይስጡ ግሥ "ማወቅ" የተለያዩ ፍችዎች እነማናቸው?
3. ቁጥር 4ን በራስህ ቃላት አብራራ።
4. ቁጥር 6 ላይ ያሉት "ብዙዎች" እነማናቸው?

# መዝሙር 5
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ከክፉ ለመጠበቅ ጸሎት<br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>"ለመዘምራን አለቃ፤ በዋሽንት፥ የዳዊት መዝሙር" | የምሪት ጸሎት | ከግል ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት (ሰቆቃ) | ለመጠበቅ ጸሎት | የማለዳ ጸሎት |
| 5:1-3 | 5:1-3 | 5:1-3 | 5:1-3 | 5:1-2<br>5:3 |
| 5:4-7 | 5:4-6 | 5:4-6 | 5:4-6 | 5:4-5ሀ<br>5:5ለ-6 |
| | 5:7-8 | 5:7-8 | 5:7-8 | 5:7 |
| 5:8-10 | | | | 5:8 |
| | 5:9-10 | 5:9-10 | 5:9-10 | 5:9<br>5:10 |
| 5:11-12 | 5:11-12 | 5:11-12 | 5:11-12 | 5:11<br>5:12 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 5፡1-3**
**[1]አቤቱ፥ ቃሌን አድምጥ፥**
**ጩኸቴንም አስተውል**
**[2]የልመናዬን ቃል አድምጥ፥ ንጉሤና አምላኬ ሆይ፥**
**አቤቱ፥ ወደ አንተ እጸልያለሁና።**
**[3]በማለዳ ድምፄን ትሰማለህ፥**
**በማለዳ በፊትህ እቆማለሁ፥ እጠብቃለሁም።**

**5፡1-2** ይህ ጸሎት የሚጀምረው በሦስት ተተኳሪዎች ነው።
1. ቃሌን አድምጥ — ቢዲቢ 24፤ ኬቢ 27፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
2. ጩኸቴንም አስተውል – ቢዲቢ 106፣ ኬቢ 122፣ *ተተኳሪ* ("ጩኸት" ቢዲቢ 211፣ እዚህጋ ብቻና መዝ. 39:3፣ "በጥልቅ ማሰብ")
3. የጩኸቴንም ድምጽ አስተውል – ቢዲቢ 904፣ ኬቢ 1151፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

እነዚህ በመዝሙረኛው በኩል ያለውን እግዚአብሔር አይሰማም የሚለውን ፍራቻ አይወክሉም፣ የዕብራይስጥን ትይዩነት እንጂ።

**5፡1 "ጌታ ሆይ"** የስሞችን ትይዩነት ተገንዘብ።

1. ጌታ ሆይ (ያህዌ፣ ዘጸ. 3፡14)
2. ንጉሤ (የቃል አወቃቀሩ የመጣው ከ1 ሳሙ. 8:7፣ መዝ. 84:3 ነው፣ ራቢዎች ኋላ ላይ ያህዌን "የዩኒቨርስ ንጉሥ" ብለው ጠርተውታል)
3. አምላኬ (ከታች ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)

ለቁ. 3 በርካታ የቃላት መልኮች አሉ ለ"ለአምላክ/አማልክት።" መልካም ምሳሌ የሚሆነው ዘዳግም 32 ነው።

1. ቁ. 3፣15 – הלא (ኤሎሀ፡ ቢዲቢ 42-43፣ መዝ. 5:2)
2. ቁ. 4፣18፣21 – לא (ኢ*l*፡ ቢዲቢ 41-42፣ መዝ. 5:4)
3. ቁ 17 – אלהים (ኤሎሂም፡ ቢዲቢ 43-44፤ ዝከ. 5:10)

ሁሉም የተመሠረቱት ኤል ላይ ነው፣ እሱም ኃይልና ብርታትን የሚገልጽ። ቅኔ ላይ ሁሉም በተለዋዋጭ መልኩ ጥቅም ላይ ይውላሉ።

**5፡3** ይህ መዝሙር የሚያመለክተው የማለዳ ጸሎትን ነው። ለድኅረ-ስደት አይሁድ በርካታ ጊዜዎች በቀን ውስጥ ተበጅተዋል፣ ጸሎት የሚቀርብበት።

1. በማለዳ መሥዋዕት ጊዜ፣ 3 ሰዓት አካባቢ። (እሱም መዝ. 46፡5ለ ሊጠቅስ ይችላል)
2. ቀትር ላይ
3. በማታ መሥዋዕት ጊዜ፣ 9 ሰዓት አካባቢ

ይህ ታማኝ ተከታይ ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆንበትን ጊዜ በቀን ውስጥ አዋቅሯል። እሱም እግዚአብሔር እንደሚሰማና ምላሽ እንደሚሰጥ አምኗል (ማለትም፣ "በጉጉት እጠብቃለሁ" ቁ. 3ለ፣ ቢዲቢ 859 I፣ ኬቢ 1044፣ ያልተጠናቀቀ)።

የየቀኑ መሥዋዕት፣ በማደሪያው ድንኳን ላይ (ዘጸ. 29:38-42)፣ ኋላም በመቅደስ፣ በየማለዳውና ምሽቱ ይሆናል። እነርሱም "የማይቋረጡ" ተብለው ተጠርተዋል። እነዚህ የተለዩ ጊዜያቶች ነበሩ፣ ወደ ያህዌ ለመቅረብ።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"አዝዛለሁ"** |
| **አኪጀት** | **"አዝዛለሁ"** |
| **አየተመት** | **"አውጃለሁ"** |
| **አእቅ** | **"አቀርባለሁ"** |
| **አኢመቅ** | **"እኖራለሁ"** |
| **LXX** | **"አቀርባለሁ"** |

ይህ ግሥ (ቢዲቢ 789፣ ኬቢ 884፣ ያልተጠናቀቀ) ሰፊ የፍቾ መስክ አለው፣ ነገር ግን በመሠረቱ ፍችው "አንድን ነገር ማስተካከል" ነው። እዚህ ሊሆን የሚችለው (1) ቃላትን ወይም (2) መሥዋዕት።

▣ ***"በጉጉት* እጠብቃለሁ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 859፣ ኬቢ 1044፣ ያልተጠናቀቀ) የሚያመለክተውም አንድን ነገር ተስፋ አድርጎ መጠበቅን ነው፣ እዚህ ያህዌ ለመዝሙረኛው ጥያቄ ምላሽ እንዲሰጥ (ሰቆ. 4:17፤ ሚኪያስ 7:7፤ ዕን. 2:1)።

**መዝሙር ፡ 5፡4-7**

**4አንተ በደልን የማትወድድ አምላክ ነህና**
**ክፉ ከአንተ ጋር አያድርም።**
**5በከንቱ የሚመኩ በዓይኖችህ ፊት አይኖሩም**
**ክፉ አድራጊዎችን ሁሉ ጠላህ።**
**6ሐሰትን የሚናገሩትን ታጠፋቸዋለህ**
**ደም አፍሳሹንና ሸንጋዩን ሰው እግዚአብሔር ይጸየፋል።**
**7እኔ ግን በምሕረትህ ብዛት ወደ ቤትህ እገባለሁ**
**አንተን በመፍራት ወደ ቅድስናህ መቅደስ እሰግዳለሁ።**

**5፡4-6** መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይገልጻል (ኤል፣ לא፣ ማስታወሻ ተመልከት 5:1 ላይ)።

1. በበደል እንደማይደሰት አምላክ
2. ክፉ ከአንተ ጋር አያድርም (ቋሚ ማደሪያ) (ያዕቆብ 1:17 ሥነ-መለኮታዊ ትይዩ ይመስለኛል)
3. በከንቱ የሚመኩ በዓይኖችህ ፊት አይኖሩም (መዝ. 1፡5)
4. ክፉ አድራጊዎችን ሁሉ ጠላህ
5. ሐሰትን የሚናገሩትን ታጠፋቸዋለህ
6. ደም አፍሳሹንና ሸንጋዩን ሰው ትጠየፈዋለህ

**5፡5 "ጠላህ"** ይህ ለእኛ አስደንጋጭ ነው — ማለትም ያህዌ፣ ፈጣሪ፣ ከሰዎች ሁሉ ጋር ኅብረትን የሚፈልግ፣ "ሲጠላ" (ቢዲቢ 971፣ ኬቢ 1338፣ የተጠናቀቀ)። መጽሐፍ ቅዱስ የሰውን ቃላት ይጠቀማል፣ መለኮትን ለመግለጽ። ይህም ዘወትር ተቃርኖን ይፈጥራል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 2፡4-6 ላይ፣ ሰዋዊነት።

እሱ "በአምሳሉ የተሠሩትን" ይወዳል (ዘፍ. 1፡26-27) ተቃራኒ ሁኔታን ይፈጥራል፣ እርስ በርሳቸው በአጥፊ መንገዶች ሲቀባበሉ!

**5፡7** *ታማኝ ካልሆነው ተከታይ በተቃራኒው፣ መዝሙረኛው ያውቃል፣ የያህዌን "የተትረፈረፈ ደግነት" (መዝ. 6፡4ለ)፣ እሱም በማደሪያው ድንኳን/በመቅደሱ በፍርሃት ያመልከዋል።*

"ደግነት" የሚለው ቃል የአአመመቅ የመተርጎሚያ መንገድ ነው፣ ኃይለኛውን የኪዳን ቃል *ሄሰድ* (ቢዲቢ 338)።

## ልዩ ርዕስ፡ ደግነት (ሄሰድHESED)

ይህ ቃል ሰፊ የፍቺ መስክ አለው። ቢዲቢ በዚህ መልኩ ይመድበዋል (338-339)፡

ሀ. ከሰው ልጆች ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ሲውል

1. ለሰው ሁሉ ደግነት (ምሳ. 1ኛ ሳሙ. 20:14፤ II ዜና. 24:22)
2. ለደሀና ለችግረኛ ደግነት (ምሳ. ሚክ. 6፡8)
3. ማዘን (ኤር. 2፡2፤ ሆሴ. 6፡4)
4. ገጽታ (ኢሳ. 40፡6)

ለ. ከእግዚአብሔር ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ሲውል

1. የኪዳን ታማኝነት እና ፍቅር
   ሀ. "ከጠላቶችና ከችግሮች በመዋጀት" (ምሳ. ኤር. 31:3፤ እዝራ 27:28፤ 9:9)
   ለ. "ከሞት ሕይወትን መመለስ" (ምሳ. ኢዮብ 10:12፤ መዝ. 86:13)
   ሐ. "መንፈሳዊ ሕይወትን ለማቀላጠፍ" (ምሳ. መዝ. 119:41፣76፣88፣124፣149፣150)
   መ. "ከኃጢአት ለመቤዠት" (መዝ. 25:7፤ 51:3)
   ሠ. "ኪዳኖቹን ለመጠበቅ" (ምሳ. 2ኛ ዜና. 6:14፤ ነህ. 1:5፤ 9:32)
2. መለኮታዊ አስተዋጽዖን ለመግለጽ (ምሳ. ዘጸ. 34፡6፤ ሚክ. 7፡20
3. የእግዚአብሔር ደግነት
   ሀ. "የተትረፈረፈ" (ምሳ. ነህ. 9:17፤ መዝ. 103:8)
   ለ. "መጠነ- ታላቅ (ምሳ. ዘጸ. 20:6፤ ዘዳ. 5:10፤ 7:9)

   ሐ. "ዘላለማዊ" (ምሳ. 1ኛ ዜና. 16:34፣41፤ II ዜና. 5:13፤ 7:3፣6፤ 20:21፤ ዕዝራ 3:11)
4. የደግነት ድርጊቶች (ምሳ. 2ኛ ዜና. 6:42፤ መዝ. 89:2፤ ኢሳ. 55:3፤ 63:7፤ ሰቆ. 3:22)

▣ ***"መቅደስ"*** በዳዊት ዘመን ምንም መቅደስ አልነበረም! ነገር ግን ተመሳሳይ ቃል (ቢዲቢ 228) 1 ሳሙ.1:9 እና 3:3 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ለማደሪያ ድንኳን።

***መዝሙር ፡ 5፡8-10***

**8 አቤቱ፥ ስለ ጠላቶቼ በጽድቅህ ምራኝ**
***መንገዴን በፊትህ አቅና።***
**9 በአፋቸው እውነት የለምና፥**
**ልባቸውም ከንቱ ነው**
**ጕሮሮአቸው የተከፈተ *መቃብር* ነው**
**በምላሳቸው ይሸነግላሉ።**
**10 አቤቱ፥ ፍረድባቸው፥**
**በምክራቸውም ይውደቁ**
**ስለ ክፋታቸውም ብዛት አሳድዳቸው፥**
**እነርሱ ዐምፀውብሃልና።**

**5፡8** ይህ የመዝሙረኛው ጸሎት ይዘት ነው፣ ቁ. 1-2 ላይ የተጠቀሰው።

1. *ምራኝ* (ተተኳሪ) በጽድቅህ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡5 ላይ)
2. *መንገድህን* ቀጥተኛ/አሙቺ አድርግልኝ (*ኬቲብ፣ ሂፊል* አለው፣ *ቁሪ፣ ፒይል* ተተኳሪ ሲኖረው፣ አእት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 854፣ ቁ. 4) በፊቴ ("ጽድቅ" እና "ቀጥተኛ" የሚሉት ቃላት ሥነ-መለኮታዊ ግንኙነት አላቸው)

**5፡9** *መዝሙረኛው የጠላቶቹ ቃላትና ድርጊት አሳስቦታል ("ጠላቶች፣" ቁ. 8፣ ቢዲቢ 1004)።*

1. በሚናገሩት ነገር ምንም ርግጠኛ/እውነት የለም
2. ውስጣዊ ማንነታቸው ራሱ ጥፋት ነው
3. ጕሮሯቸው የተከፈተ መቃብር ነው
4. ሸንጋይ/ለስላሳ አንደበት ናቸው (መዝ. 12፡2)

ጳውሎስ ይህንን ቁጥር ይጠቅሳል፣ በአኪ. ጽሑፎች መግለጫ ላይ፣ እነርሱም የወደቀውን ሰው ልጅ ባሕርይ የሚያንጸባርቁ ሮሜ 3፡ 10-18 (በተለይም፣ ቁ. 13)።

**5፡10** *መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይጠይቃል፣ በጠላቶቹ ላይ እንዲነሣ፣ ከቃላቸውና ከድርጊታቸው የተነሣ።*

1. ይኮነኑ – ቢ.ዲ.ቢ. 79፣ ኬቢ. 95፣ *ሂፊል ተተኳሪ* (የመጽደቅ ተቃራኒ)
2. በገዛ *ሥራቸው* ይውደቁ – ቢ.ዲ.ቢ. 656፣ ኬቢ. 709፣ ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. በበዛው *መተላለፋቸው* ይጣሉ – ቢ.ዲ.ቢ. 623፣ ኬቢ. 673፣ *ሂፊል ተተኳሪ* (ማለትም፣ ያህዌ ከሚገኝበት፣ ከአምልኮ ስፍራ፣ መዝ. 5:7 ወይም ከችሎት መዝ. 5:5)
4. እነርሱ ባንተ ላይ *ዓምጸውብሃልና* – ቢ.ዲ.ቢ. 598፣ ኬቢ. 632፣ የተጠናቀቀ

መዝሙረኛው የተጠቀመባቸውን የተለያዩ ቃላት ተገንዘብ፣ ጠላቶቹን ለመግለጽ።

1. ክፉ፣ ቁ. 4
2. ትምክህተኛ፣ ቁ. 5
3. በደልን የሚሠሩ፣ ቁ. 5
4. ሐሰትን የሚናገሩ፣ ቁ. 6
5. ደም አፍሳሽ ሰዎች፣ ቁ. 6
6. አሳች ሰዎች፣ ቁ. 6
7. ጠላቶች (ማለትም፣ አድብተው የሚጠብቁ)፣ ቁ. 8
8. ምንም እውነተኛ ያልሆኑ፣ ቁ. 9
9. ጥፋትን የተሞሉ፣ ቁ. 9
10. ውሸተኞች፣ ቁ. 9
11. ተላላፊዎች፣ ቁ. 10
12. ዐመጸኞች፣ ቁ. 10

***መዝሙር ፡ 5፡11-12***

**11በአንተ የሚታመኑት ሁሉ ግን ደስ ይላቸዋል**
**ለዘላለሙ ደስ ይላቸዋል፥**
**እነርሱንም ትጠብቃለህ**
**ስምህንም የሚወድዱ ሁሉ በአንተ ይመካሉ።**
**12አንተ ጻድቁን ትባርከዋለህና አቤቱ፥**
**እንደ ጋሻ በሞገስ ከለልኸን።**

**5፡11-12** ከክፉ ጠላት በተቃራኒው፣ መዝሙረኛው አሁን ታማኝ ተከታዮችን ይገልጻል (ማለትም፣ የብዙ ቁጥር፣ የአንዱ ጸሎትና ልምምድ የሁሉም መግለጫ ሆነ)።

1. እነርሱ ያህዌን *መተማመኛ* አድርገዋል
2. እነርሱ በያህዌ ይደሰታሉ
3. እነርሱ በእርሱ መጠጊያ ያደርጋሉ (እንደማስበው፣ ይህ የሚያመለክተው የሴቷን ወፍ ዘይቤ ነው፣ ሩት 2:12፤ መዝ. 17:8፤ 36:7፤ 57:1፤ 61:4፤ 63:7፤ 91:1፣4፤ ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት)
4. እነርሱ የእርሱን ስም ይወዳሉ እጅግም ደስ ይላቸዋል (ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት)

በዚህ እይታ መሠረት፣ ያህዌ

1. ያስጠጋቸዋል
2. ይባርካቸዋል
3. እንደ ጋሻ ይከልላቸዋል (1 ሳሙ. 23፡26)

አንዱ በታማኝ ተከታዮች እና በማይታመኑ ተከታዮች መካከል ያለውን ልዩነት በፍሬያቸው ያውቃል (ማቴ. 7፡15-22)!

## ልዩ ርዕስ፡ ጥላ ለጥበቃና ለክብካቤ ዘይቤነት

"ጥላ" የሚለው ፈሊጥ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) የተለመደ ነው። ምሳሌዎቹን ከመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ተመልከት።

1. ለጥበቃ ፈሊጥ፣ ኢሳ. 16:3፤ 30:2-3፤ ሰቆ. 4:20
2. "ለእጅ ጥላ" ፈሊጥ፣ መዝ. 121:5፤ ኢሳ. 49:2፤ 51:16
3. "ለጣርያ ጥላ" ፈሊጥ፣ ዘፍ. 19:8
4. "ለእግዚአብሔር የተለየ ደመና ጥላ" ፈሊጥ፣ ዘጸ. 13:21-22፤ 14:19,20,24፤ ኢሳይያስ 4:6፤ 25:4-5፤ 32:1-2
5. "ለክንፍ ጥላ" ፈሊጥ፣ መዝ. 17:8፤ 36:7፤ 57:1፤ 61:4፤ 63:7፤ 91:1,4 (ተመሳሳይ ዘይቤዎች ዘዳ. 32:10-11፤ ሩት 2:12፤ ኢሳ. 31:5፤ ማቴ. 23:37፤ ሉቃስ 13:34 ላይ)
6. "ለዛፍ ጥላ" ፈሊጥ፣ መሳ. 9:15፤ ሕዝ. 17:23፤ 31:6,17፤ ዳን. 4:12፤ ሆሴዕ 14:7

### ልዩ ርዕስ፡ የያህዌ "ስም"

"የስም" አጠቃቀም ለያህዌ ለራሱ ምትክነት፣ ከጸአ. 23፡20-33 ከ "መልአክ" አጠቃቀም ጋር ትይዩ ነው፣ እሱም "ስሜ በእርሱ ላይ ነው" ያለው። ይህ የስም መተካት በ "ክብሩ" አጠቃቀም ላይ ሊታይ ይችላል (ምሳ. ዮሐንስ 1፡14፤ 17፡22)። ሁሉም የሚሞክሩት የያህዌን አካላዊ ሰዋዊ መገኘት ለማለዘብ ነው (ዘጸ. 3፡13-16፤ 6፡3)። ያህዌ በርግጥ በሰውኛ ቃላት ተነግሯል፣ ነገር ግን ደግሞ የሚታወቀው በፍጥረት ሁሉ በመንፈሳዊነት መገኘቱ ነው (1 ነገሥ. 8:27፤ መዝ. 139:7-16፤ ኤር. 23:24፤ ሐዋ. 7:49 ኢሳ. 66፡1ን ይጠቅሳል)።

በርካታ ምሳሌዎች አሉ፣ የያህዌን መለኮታዊ ሕላዌ እና አካላዊ መገኘት ስለሚወክለው "ስም"።

1. ዘዳ. 12:5፤ 2 ሳሙ. 7:13፤ 1 ነገ. 9:3፤ 11:36
2. ዘዳ. 28:58
3. መዝ. 5:11፤ 7:17፤ 9:10፤ 33:21፤ 68:4፤ 91:14፤ 103:1፤ 105:3፤ 145:21
4. ኢሳ. 48:9፤ 56:6
5. ሕዝ. 20:44፤ 36:21፤ 39:7
6. አሞጽ 2:7
7. ዮሐንስ 17:6,11,26

"መጥራት" (ማለትም፣ ማምለክ) የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ፣ የያህዌን ስም፣ ቀደም ብሎ በዘፍጥረት ላይ ታይቷል።

1. 4፡26፣ የሴት ዘር
2. 12፡8፣ አብርሃም
3. 13፡4፣ አብርሃም
4. 16፡13፣ አጋር
5. 21፡33፣ አብርሃም
6. 26፡25፣ ይስሐቅ

በዘጸአትም፡

1. 5፡22-23፣ በስምህ ይናገራሉ
2. 9፡16፣ ስሜን በዓለም ሁሉ ያሳያሉ (ሮሜ. 9፡17)
3. 20፡7፣ የጌታ የአምላክህን ስም በከንቱ አታንሣ (ሌዋ. 19:12፤ ዘዳ. 5:11፤ 6:13፤ 10:20)
4. 20:24, ስሜ እንዲጠራ ባዘዝኩበት ስፍራ (ዘዳ. 12:5፤ 26:2)
5. 23:20-21, መልአክ ("ስሜ በእርሱ ላይ አለና")
6. 34:5-7, ሙሴ ጠራ (ወይም "ተጣራ") የእግዚአብሔርን ስም። ይህ ከእፍኝ ሙሉ ጽሑፎች አንዱ ነው፣ የያህዌን ባሕርይ የሚገልጽ (ነህ. 9:17፤ መዝ. 103:8፤ ኢዩኤል 2:13)

አንዱን በስሙ ማወቅ ቅርበትን ያመላክታል (ዘጸ. 33፡12)፤ ሙሴ የያህዌን ስም ያውቃል፣ እናም 33፡17 ላይ፣ ያህዌም የሙሴን ስም ያውቃል። ይህ ዐውደ-ጽሑፍ ሙሴ የእግዚአብሔርን ክብር እንዲያይ የፈለገበት ነው (ዘጸ. 33፡18)፣ እግዚአብሔር ግን "የእርሱን መልካምነት" እንዲያይ ፈቀደለት (ዘጸ. 33፡19)፣ እሱም ከ "ስሙ" ጋር ትይዩ የሆነ (ቁ. 19)።

እስራኤላውያን የከነአንን ጣዖታት "ስሞች" እንዲያጠፉ ነበር፣ (ዘዳ. 12፡3) እና የእርሱን እንዲጠሩ (ዘዳ. 6:13፤ 10:20፤ 26:2) ስሙ እንዲያድርበት በመረጠው ልዩ ስፍራ (ዘጸ. 20:24፤ ዘዳ. 12:5,11,21፤ 14:23,24፤ 16:2,6,11፤ 26:2)።

ያህዌ ሁለንተናዊ ዓላማ አለው፣ ስሙን በተመለከተ።

1. ዘፍ. 12፡3
2. ዘጸ. 9፡16
3. ዘጸ. 19፡5-6
4. ዘዳ. 28፡10፣58
5. ሚክያስ 4፡1-5

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙር 4 እንደ ምሽት መዝሙር እንዲሁም መዝሙር 5 ማለዳ መዝሙር ለምን ተቆጠረ?
2. ያህዌ ያደረገውን ዘርዝር፣ ከቁጥር 4-6።
3. የእምነት ሕይወት እንደ መንገድ/ፈለግ/ጎዳና ነው የተገለጸው። ለምን?
4. ክፉዎችን ዘርዝር፣ ከቁጥር 4-6 እና 9-10።

## መዝሙር 6
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የምሕረት ጸሎት በችግር ጊዜ<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>"ለመዘምራን አለቃ፤ ስምንት አውታር ባለው በገና። የዳዊት መዝሙር" | የእምነት ጸሎት በጭንቀት ጊዜ | ከጽኑ ሕመም ለመፈወስ ጸሎት | የዕርዳታ ጸሎት በችግር ጊዜ | የዕርዳታ ጸሎት በመከራ ጊዜ |
| 6:1-3 | 6:1-3 | 6:1-3 | 6:1-3 | 6:1-3 |
| 6:4-5 | 6:4-5 | 6:4-5 | 6:4-5 | 6:4-5 |
| 6:6-7 | 6:6-7 | 6:6-7 | 6:6-7 | 6:6-8ሀ |
| 6:8-10 | 6:8-10 | 6:8-10 | 6:8-10 | 6:8ለ-10 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 6፡1-3**
**1አቤቱ፥ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፥**
**በመዓትህም አትገሥጸኝ።**
**2ድውይ ነኝና አቤቱ፥ ማረኝ**
**አጥንቶቼ ታውከዋልና ፈውሰኝ።**
**3ነፍሴም እጅግ ታወከች**
**አንተም አቤቱ፥ እስከ መቼ ድረስ ነው?**

**6፡1** ሁለት ተተኳሪዎች አሉ፣ እንደ ተጽዕኗዊ ጥቅም ላይ የዋሉ።
1. *መገሠጽ* — ቢዲቢ 406፣ ኬቢ 410፣ *ሂፊል* በአሉታዊ፣ መዝ. 38:1
2. *መቅሠፍ* – ቢዲቢ 415፣ ኬቢ 418፣ *ፒይል* በአሉታዊ

ይህ የንስሐ መዝሙር ነው፣ እንደ መዝሙር 32፣ 38፣ 51፣ 102፣ 130፣ እና 143። የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 1289) እንደሚለው ይህ የዕርዳታ ጸሎት መዝሙር የአይሁድ ሕዝቦች የማለዳ ጸሎት ሥርዓት ሆኗል።

▣ ***"በቍጣህ... በመዓትህ"*** *መዝሙሩ ያህዌ ለምን እንደተቆጣ አይገልጽም። እሱ የብኪ ሥነ-መለኮት የአንዱን ምክንያታዊነት ሊያንጸባርቅ ይችላል። መዝሙረኛው ጠላቶች አሉት፣ ያህዌ ፈቅዶላቸዋል/ልኳቸዋል (ዝከ. ቁ. 3)። የሕይወት ሁኔታዎች ሊሆኑ የሚችሉት*

1. የኃጢአት ቅጣት (መዝ. 41:4)
2. ሕይወት በወደቀው ዓለም (መዝ. 147:3)
3. እምነትን የማጠናከሪያ መንገዶች (1 ቆሮ. 10:13፤ ዕብ. 5:8)

ሆኖም፣ አንዱ የትኛው እንደሆነ ፈጽሞ ሊያውቅ አይችልም፣ ስለዚህ ንስሐ ግባ እምነትም ይኑርህ!

**6:2-3** *"መታወክ"* እንዴት እንደሆነ ተገንዘብ (ቢዲቢ 96፣ ኬቢ 111፣ *ኒፋል የተጠናቀቀ*) ከሁለቱም ጋር እንደሚገናዘብ

1. አጥንቶቼ (ቢዲቢ 782)፣ ቁ. 2
2. ነፍሴ (*ኔፈሽ*፣ ቢዲቢ 659፣ ዝከ. ቁ. 4)፣ ቁ. 3 (መዝ. 3:2 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት)

እነዚህ ሁለቱ የሰውን ውስጣዊ ሕይወት እና ሐሳብ አመላካች መንገዶች ናቸው። ይህ ጸሐፊ በታላቅ ጭንቀት ውስጥ ነው፣ ለምን እንደሆነም አላወቀም!

**6:2** ቁጥር 1 ያህዌ እንዳያደርግ እንደሚጠይቅ ሁሉ፣ ቁጥር 2 ያህዌን ይጠይቃል (ደግሞም ቁ. 4 ተመልከት)

1. *ማረኝ* – ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334፣ *ተተኳሪ*
2. *ፈውሰኝ* – ቢዲቢ 950፣ ኬቢ 1272፣ *ተተኳሪ*

*"ፈውስ"* የሚለው ግሥ ከአካላዊ ሕመም ጋር ብቻ ላይዛመድ ይችላል (ኒዶቲ፣ ቅጽ. 3፣ ገጽ. 1166፣ ሐ፣ ኢሳ. 1:5-6)፣ ነገር ግን የጠላቶች ጥቃት (ዝከ. ቁ. 7ለ፣ 10)። ሆኖም፣ ቁጥር 2 ክፍት አድርጎ ይተወዋል፣ ሕመም ሊሆን እንደሚችል። ሕመም ከሆነስ፣ ጠላቶች ለምን ተጠቀሱ? አንዳንዶች የሚሉት ጠላቶች በመዝሙረኛው ሕመም ላይ ቀልደውበታል (መዝሙር 102:8)። የጥንቶቹ እስራኤላውያን የሚያምኑት ኃጢአትና ሕመም እንደሚዛመዱ ነው።

**6:3** ***"እስከ መቼ"*** ይህ የግለሰብ ጩኸት ነው፣ በእግዚአብሔር አምሳል የተሠራ፣ ነገር ግን በወደቀ ሐሳብ፣ ሥጋ፣ እና ዓለም የተጠመደ (መዝ. 13:1፤ 74:10፤ 90:13)! እንደ አማኞች እግዚአብሔርን እናምናለን፣ ሁኔታዎችን ሳይሆን፣ ግን አሁንም እንጮኻለን—ለምን? መቼ ነው የሚያበቃው?

***መዝሙር ፡ 6:4-5***

**[4]አቤቱ፥ ተመለስ ነፍሴንም አድናት፥**
**ስለ ቸርነትህም አድነኝ።**
**[5]በሞት የሚያስብህ የለምና፥**
***በሲኦልም የሚያመሰግንህ ማን ነው?***

**6:4** መዝ. 6:2 ያህዌን እንደሚጠይቅ፣ ስለመዝሙረኛው (ማለትም፣ "ማረኝ... ፈውሰኝ")፣ እንዲሁ ደግሞ፣ ቁጥር 4።

1. *ተመለስ* – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ *ተተኳሪ*
2. *አድን* – ቢዲቢ 322፣ ኬቢ 321፣ *ፒይል ተተኳሪ*
3. *አድን* – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

ለጥያቄዎቹ የተሰጠው ምክንያት ለመዝሙረኛው የሚገባ ወይም የድካም ዋጋው አይደለም፣ ነገር ግን የማይለወጠው፣ ምሕረት የተሞላው የኪዳን ፈጣሪ/ተቤዢ መለኮት ባሕርይ ነው!

አንዱ ሊደነቅ ይችላል "ተመለስ" በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ምን እንደሆነ። መዝሙረኛው አስቦ ይሆን እንዴ፣ ያህዌ እንደራቀው ወይም ራሱን እንደደበቀ?

▣ ***"ቸርነት"*** ልዩ ርዕስ መዝ. 5:7 ላይ ተመልከት።

**6:5** ቁ 5 ከሞት በኋላ ስላለው የብኪ አመለካከት ይገልጻል። ሲኦል የሚታወቅበት ስፍራ ነው፣ ነገር ግን ምንም ደስታና ምስጋና የሌለበት። የሚታወቅበት ሕላዌ አጠቃላይ ጉዳይ፣ ከሥጋዊ ሞት በኋላ በቅዱስ ቃሉ እየዳበረ መጥቷል። በብኪ ፍንጮች ብቻ ነው ያሉት (ኢዮብ 14:14-15፤ 19:25-27፤ መዝ. 16:10፤ 49:15፤ 86:13፤ ኢሳ. 25:8፤ 26:19፤ ሕዝ. 37:12-13፤ ዳን. 12:1-2፤ ሆሴ. 13:14)። ሙሉው እውነት የተገለጠው 1 ቆሮንቶስ 15 ላይ ነው!

የዕብራይስጡ ሲኦል (ቢዲቢ 982) የሙታንን ስፍራ ያመለክታል። እሱም መለያው

1. ጨለማ፣ ጨፍጋጋ ስፍራ፣ ኢዮብ 10:21-22፤ መዝ. 143:3
2. መመለስ የሌለበት ስፍራ፣ ኢዮብ 10:21፤ 16:22
3. እግዚአብሔርን የማያመሰግኑበት ስፍራ፣ መዝ. 6:5፤ 30:9፤ 38:18፤ 88:10-12፤ 115:17 (ዝምታ፣ መዝ. 94:17)
4. ከእግዚአብሔር የሚለዩበት ስፍራ፣ መዝ. 88:5፤ 39:13፣ ሆኖም እግዚአብሔር እዚያ አለ፣ መዝ. 139:8፤ ምሳ. 15:11!

ልዩ ርዕስ ተመልከት: ሙታን የት ናቸው? መዝ. 1:6 ላይ።

ደራሲው በራሱ መረዳት ሲኦልን ለይቶ የገለጸው፣

1. ማስታወስ የሌለበት (ቢዲቢ 271)
2. ምስጋና የሌለበት (ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂሬል ያልተጠናቀቀ*፣ መዝ. 30:9፤ 88:10-12፤ ኢሳ. 38:18)

ቲንዳሌ የብኪ ተከታታይ ሐተታ (ቅጽ. 15፣ ገጽ. 78) በብኪ ለሲኦል ጥቅም ላይ የዋሉትን ምስያዎች ይዘረዝራል።

1. ሰፊ ጨለማ ስፍራ – ሕዝ. 32:18-32
2. ምሽግ – መዝ. 9:13፤ 107:18፤ ማቴ. 16:18
3. ጨለማ ቆሻሻ ስፍራ – ኢዮብ 10:22
4. ትልቅ አውሬ፣ ባለ ሰፊ አፍ– ኢሳ. 5:14፤ ዮናስ 2:2፤ ዕን. 2:5

እግዚአብሔር ስለ አዲስ ኪዳን ይመስገን!

**መዝሙር ፡ 6፡6-7**

**[6]በጭንቀቴ ደክሜያለሁ**
**ሌሊቱን ሁሉ አልጋዬን አጥባለሁ፥**
**በዕንባዬም መኝታዬን አርሳለሁ።**
**[7]ዓይኔ ከቍጡ ዕንባ የተነሣ ታወከች**
**ከጠላቶቼ ሁሉ የተነሣ አረጀሁ።**

**6፡6-7** መዝሙረኛው "በጠላቶቹ" የደረሰበትን አካላዊና ስሜታዊ ጥቃት ይገልጻል (ቢዲቢ 865፣ ኬቢ 1058፣ አንቀጽ፣ "ጠላትነታቸውን የሚያመለክቱ")።

1. በጭንቀት መድከም (ቢዲቢ 58)
2. መኝታ በዕንባ መራስ (ግነታዊ)

**መዝሙር ፡ 6፡8-10**

**[8]ዓመፃን የምታደርጉ ሁሉ፥ ከእኔ ራቁ፥**
**እግዚአብሔር የልቅሶዬን ቃል ሰምቶአልና።**
**[9]እግዚአብሔር ልመናዬን ሰማኝ**
**እግዚአብሔር ጸሎቴን ተቀበለ።**
**[10]ጠላቶቼ ሁሉ ይፈሩ እጅግም ይጐስቍሉ**
**ወደ ኋላቸው ይመለሱ፥ በፍጥነትም ይፈሩ።**

**6፡8-10** መዝሙረኛው ወደ አእምሯዊ ዕረፍት መጥቷል፣ በያህዌ በመታመኑ፣ ጸሎቱን ወደ ሰማው (መዝ. 28፡6)። ይህም በሦስት ትይዩ ስንኞች ይገለጻል (ማለትም፣ መዝ. 6፡8ለ፣ 9ሀ፣ 9ለ)።

ያህዌ ጸሎቱን ስለ ሰማ ጠላቶቹ

1. መራቅ ይኖርባቸዋል፣ ቁ. 8ሀ (መዝ. 119:115፤ 139:19)
2. ያፍራሉ፣ ቁ. 10 (መዝ. 71:13፣24)
3. እጅግ ይደነግጣሉ፣ መዝ. 6፡10 (ተመሳሳይ የሆነ ግሥ፣ በመዝሙረኛው ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 6፡2ለ እና 3ሀ ላይ)
4. ወደ ኋላ ይመለሳሉ፣ ቁ. 10 (ተመሳሳይ የሆነ ግሥ፣ ለያህዌ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 4 ላይ፣ እዚህ ግን ወደ ሲኦል ስለመሄድ ይሆናል፣ ኢዮብ 34:15፤ መዝ. 9:18፤ መክ. 3:20፤ 5:15፤ 12:7)
5. በድንገት ያፍራሉ (ተመሳሳይ ግሥ እንደ ቁ. 10ለ፣ መዝ. 73:19)

ቁጥር 2-5 ሁሉም ያልተጠናቀቁ ናቸው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ። መዝሙረኛው የያህዌን መገኘት ሽቷል፣ ብሎም የጠላቶቹን አለመገኘት! እነርሱ በእርሱ ላይ ለማድረግ የሞከሩት በእነርሱ ላይ ሆኗል! ይህ ጽሑፋዊ አወቃቀር (ማለትም፣ የተገላቢጦሽ) በብኪ የተለመደ ነው። ሰዎች የሚጠብቁት ዘወትር ያህዌ ሊያመጣ ካለው ተቃራኒውን ነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልስህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ሲኦልን ከብኪ አስተሳሰብ አኳያ ግለጽ።
2. "ማፈር" ምን ማለት እንደሆነ ከብኪ ይዘት አኳያ ግለጽ።
3. የያህዌ ቁጣና መዓት ከኃጢአተኛ እና ከታማኝ ተከታይ ጋር እንዴት ይዛመዳል?

# መዝሙር 7
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ መዝሙረኛውን እንዲከላከል ተለመነ በከፉ ላይ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>"የዳዊት መዝሙር ለጌታ የዘመረው ስለ ብንያማዊ ሰው ስለ ኩዝ" | ከጠላቶቹ እንዲታደገው ጸሎትና ምስጋና | ከግል ጠላቶች እንዲታደገው ጸሎት (ሰቆቃወ) | ስለ ፍትሕ ጸሎት | የስደት ጊዜ የጻድቅ ጸሎት |
| 7:1-2 | 7:1-2 | 7:1-2 | 7:1-2 | 7:1-5 |
| 7:3-5 | 7:3-5 | 7:3-5 | 7:3-5 | |
| 7:6-11 | 7:6-8 | 7:6-8 | 7:6-9 | 7:6-8a |
| | | | | 7:8b-9 |
| | 7:9-10 | 7:9-11 | | |
| | | | 7:10-13 | 7:10-12a |
| | 7:11-13 | | | |
| 7:12-16 | | 7:12-16 | | |
| | | | | 7:12b-14 |
| | 7:14-16 | | 7:14-16 | |
| | | | | 7:15-16 |
| 7:17 | 7:17 | 7:17 | 7:17 | 7:17 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 7፡1-2**

**[1]አቤቱ አምላኬ፥ በአንተ ታመንሁ**
**ከሚያሳድዱኝ ሁሉ አድነኝና አውጣኝ፥**
**[2]ነፍሴን እንደ አንበሳ ነጥቀው እንዳይሰብሩዋት፥**
**የሚያድንና የሚታደግ ሳይኖር።**

**7፡1 “*በአንተ ታመንሁ*”** *ይህ ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 340፣ ኬ.ቢ. 337) የተጠናቀቀ ነው፣ እሱም የተፈጸመን ወይም የተበጀ ድርጊትን የሚገልጽ። *መዝሙረኛው የሚታመንበትን ፈልጓል፣ እየፈለገም ነው (ማለትም፣ መጠጊያ፣ ክብካቤ፣ ሰጪ) ከያህዌ።*

▣ *መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይጠይቃል*

1. እንዲያድነው – ቢ.ዲ.ቢ. 446፣ ኬ.ቢ. 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
2. እንዲታደገው – ቢ.ዲ.ቢ. 664፣ ኬ.ቢ. 717፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

በእርሱ ላይ በመታመኑ (ቢ.ዲ.ቢ. 340፣ ኬ.ቢ. 337፣ የተጠናቀቀ)። *ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ መዝ.* 2:12፤ 5:11፤ 7:1፤ 11:1፤ 16:1፤ 17:7፤ 18:2፣30፤ 25:20፤ 31:1፣19፤ 34:8፣22፤ 36:7፤ 37:40፤ 57:1፤ 61:4፤ 64:10፤ 71:1፤ 118:8፣9፤ 141:8፤ 144:2። *ያህዌ ብቻ ነው የመጠበቂያና የዕረፍት ትክክለኛ ስፍራ!*

**7:2** *መዝ.* 7:1 ላይ የመዝሙረኛው ተቃራኒዎች “የሚያሳድዱኝ እነርሱ” በሚል ተጠርተዋል። ቁጥር 2 ላይ እነርሱ የተገለጹት እንደ *ሥጋ*-በል አውሬ ነው (*መዝ.* 57:4)።

1. *መቅደድ*– ቢ.ዲ.ቢ. 382፣ ኬ.ቢ. 380፣ *ያልተጠናቀቀ*፣ *መዝ.* 17:12
2. *መንጠቅ* – ቢ.ዲ.ቢ. 830፣ ኬ.ቢ. 973፣ *አንቀጽ*
3. *የሚያድን ሳይኖር* — *ይህ የቁ. 1 ተቃራኒ ነው፣ መዝሙረኛው ያህዌ እንዲታደገው የሚለምንበት። ማንም ሳይሆን እግዚአብሔር ብቻ ይችላል!*

*መዝሙረኛው አንድም ኃይለኛ ዘይቤዎችን ተጠቅሟል ወይም ከጠላቶቹ የሚሰነዘርበትን አካላዊ ጽኑ ጥቃት ፈርቷል።*

## ልዩ ርዕስ: አናብስት በብሉይ ኪዳን

ብዙ ጊዜ የግለሰብ ወይም የሕዝብ ኃይል እንደ አንበሳ ይገለጻል፣ አድኖ ለሚበሉት እንስሳት ንጉስ፡፡

1. ይሁዳ፣ዘፍጥ49:9፤ሚክ5:8
2. ያህዌ በእስራኤል ፋንታ፣ዘኁል24:9፤እሳ31:4፤ 35:9፤ሆሴ11:10
3. እስራኤል እንደ ተሸነፈ አንበሳ፣ሕዝ19
4. የዳን ጎሳ፣ዘዳግ33:22
5. የዳዊት ጉልበት በአናብስት ላይ፣ I ሳሙ17:34-37
6. ሳሙኤል እና ዮናታን፣ II ሳሙ1:23
7. የሰሎሞን ዘፈን ጠባቂዎች ተምሳሌት፣ I ስ10:19-20
8. እግዚአብሔር አንበሳን እንደ ቅጣት ይጠቀምበታል፣ I ስ13፣20፤ II ስ17:25-26፤እሳ15:9፤በኢዮብ 4:10 ውስጥ ተምሳሌት፤ ኤርም2:30፤ 49:19፣44፤ ሰቆቃ :10፤አሞ3:4፣8፣12፤ 5:19፤ሆሴ5:14፤ 13:7-8፤ ነህ2:11-12
9. እግዚአብሔር ከሚያድነው የዳዊት ጠላቶችን ይገልጻል፣መዝ7:2፤ 10:9፤ 17:12፤ 22:13፣21
10. ለማይታወቅ ክፉ ተምሳሌት ነው፣ምሳሌ22:13፤ 26:13፤ 28:15
11. የባቢሎንን ወታደር ለመግለጽ ተጠቅሞበታል፣ ኤር4:7፤ 49:19-22፤ 51:38
12. የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚቃወሙ የስታት ወታደር፣ኤርም5:6፤ 25:32-38፤ 50:17፤ኢዮኤል 1:6
13. የእግዚአብሔር ሕዝብ አምላካአቸውን እንዴት ማየት እንዳለባቸው፣ኤር 12:8
14. የእግዚአብሔር መሪዎች ሕዝባቸውን እንዴት ማየት እንዳለባቸው፣ሕዝ 22:25፤ ሶፎ3:3
15. የተቆጣ ንጉስ ተምሳሌት፣ምሳሌ19:12፤ 20:2
16. የጻድቅ ተምሳሌት፣ምሳሌ28:1፤
17. የመሲይው ተምሳሌት፣ዘፍጥ49:9፤ ረአይ 5:5

በኤርምያስ ውስጥ በ #11 እና #12ላይ፣ዳንኤል ለባብሎን ወታደር እንደ ፈጣን አንበሳ ተምሳሌት የወሰደው የታወቀ ነው፡፡ ለም ግዛቶች የሆኑ(Empires of the Fertile Crescent) ብዙ ጊዜ አንበሳን ለሕዝብ ለማስመሰል ይጠቀሙበታል፡፡

## የቃልና የሐረግ ጥናት

***መዝሙር ፡ 7፡3-5***

**[3]አቤቱ አምላኬ፥ እንዲህስ ካደረግሁ፥**
**ዓመፃም በእጄ ቢኖር፥**
**[4]ክፉ ላደረጉብኝም ክፉን መልሼላቸው ብሆን፥**
**ጠላቴንም በከንቱ ገፍቼው ብሆን፥**
**[5]ጠላት ነፍሴን ያሳድዳት ያግኛትም፥**
**ሕይወቴንም በምድር ላይ ይርገጣት፥**
**ክብሬንም በትቢያ ላይ ያዋርዳት። ሴላህ**

**7፡3-5** መዝሙረኛው መላምታዊ የሆነ ትይዩ ሁኔታዎችን ያሳያል።

1. ይህን ባደርግ (ግን "ይህ" ተለይቶ አልተቀመጠም)
2. ዓመፃም በእጄ ቢኖር (ማለትም፣ ድርጊቶች፣ ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ
3. ለባልንጀራዬም ክፉ መልሼ ብሆን (ይህ በደንብ የሚታወቀው ምሳሌ ነው፣ ምሳ. 20፡22፤ 24፡29፤ ሮሜ. 12፡17)
4. ባልንጀራዬንም በከንቱ ገፍቼው ብሆን

ከእነዚህ አንዳቸውም ነገሮች እውነት ቢሆኑ፣ እንግዲያውስ

1. ጠላቴ ያሳድደኝ – ቢዲቢ 922፣ ኬቢ 1191፣ ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ጠላቴ ድል ያድርገኝ – ቢዲቢ 673፣ ኬቢ 727፣ ሂፊል ተጽዕኗዊ
3. ጠላቴ ሕይወቴን ይርገጣት – ቢዲቢ 942፣ ኬቢ 1245፣ ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
4. ክብሬንም በትቢያ ላይ ያዋርዳት – ቢዲቢ 1014፣ ኬቢ 1496፣ ሂፊል ተጽዕኗዊ ("ክብር" በአንዱ የሕይወት ዋና ነገር መልኩ (መዝ. 16:9፤ 30:12፤ 57:8፤ 108:1)

ይህ ንጽሕናን ለማሳየት ቅኔአዊ መንገድ ነው!

## ልዩ ርዕስ፡ እጅ (ከሕዝቅኤል ላይ የተገለጸ)

"እጅ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 388) በርካታ ፍችዎችና አጠቃቀሞች አሉት።

1. በጥሬው (ማለትም፣ የሰው እጅ)
   ሀ. የሙሉ ሰውነት ተምሳሌት፣ ሕዝ. 3:18፤ 18:8,17፤ 33:6,8
   ለ. የሰው ደካማነት ተምሳሌት፣ ሕዝ. 7:17,27፤ 21:7፤ 22:14
   ሐ. የባዕድ ጠላቶች ተምሳሌት፣ ሕዝ. 7:21፤ 11:9፤ 16:39፤ 21:31፤ 23:9,28፤ 28:10፤ 30:12፤ 34:27፤ 38:12፤ 39:23
   መ. እጅ በቁሙ፣ ሕዝ. 8:11፤ 12:7፤ 16:11፤ 37:17,19,20
   ሠ. የሐሰተኛ መሪዎች ኃይል ተምሳሌት፣ ሕዝ. 13:21,22,23፤ 34:10
   ረ. የሕዝብ ተምሳሌት፣ ሕዝ. 23:31,37,42,45፤ 25:14፤ 27:15፤ 28:9፤ 30:10,22,24,25፤ 31:11፤ 39:3
2. የመለኮት ሰዋዊ ዘይቤ
   ሀ. የራዕይ ግብዣ፣ ሕዝ. 1:3፤ 3:14,22፤ 8:1፤ 33:22፤ 37:1፤ 40:1 (2:9 ሌላው ዘይቤ ነው – በእጅ ያለ ጥቅል)
   ለ. የያህዌ ሥልጣን በፍርድ ላይ፣ ሕዝ. 6:14፤ 13:9፤ 14:9,13፤ 16:27፤ 20:33፤ 25:7,13,16፤ 35:3፤ 39:21
   ሐ. ያህዌ ራሱ (የእርሱ አካላዊ መገኘት), ሕዝ. 20:22
   መ. የያህዌ ሥልጣን ለማዳን፣ ሕዝ. 20:34 (እሱም ቁልፍ አጠቃቀም የሚሆን ከዘጸአት፣ ዝከ. 3:20፤ 4:17፤ 6:1፤ 7:19፤ 13:3)
3. የኪሩቤል ሰዋዊ ዘይቤነት፣ ዝሕ. 1:8፤ 8:3፤ 10:7,8,12,21
4. የአጥፊ መልአክ ሰዋዊ ዘይቤነት፣ ሕዝ. 9:1-2፤ 21:11
5. የቃል መግባት ወይም መሐላ ተምሳሌት፣ ሕዝ. 17:18፤ 20:5(ሁለቴ),6,15,23,28፤ 36:7፤ 44:12፤ 47:14
6. የደስታ ተምሳሌት፣ ሕዝ. 25:6
7. የመልአክ ሰዋዊ ዘይቤነት፣ ሕዝ. 40:3,5፤ 47:3

**7፡5 "ሴላህ"** መዝ. 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻና መግቢያ ለመዝሙር፣ VIII ላይ ተመልከት።

***መዝሙር ፡ 7፡6-11***

***6አቤቱ፥ በመዓትህ ተነሥ፥***
***በጠላቶቼ ላይ በቍጣ ተነሣባቸው***
***አቤቱ አምላኬ፥ ባዘዝኸው ትእዛዝ ንቃ።***
***7የአሕዛብም ጉባኤ ይከብብሃል፥***
***በእነርሱም ላይ ወደ ከፍታ ተመለስ።***
***8እግዚአብሔር በአሕዛብ ይፈርዳል***
***አቤቱ፥ እንደ ጽድቁ ፍረድልኝ፥ እንደ የዋህነቴም ይሁንልኝ።***
***9የኃጥኣን ክፋት ይጥፋ፥ ጻድቁን ግን አቅና***
***እግዚአብሔር ልቡናንና ኩላሊትን ይመረምራል።***
***10እግዚአብሔር የጽድቅ ጋሻዬ ነው***
***ልበ ቅኖችን የሚያድናቸው።***
***11እግዚአብሔር የእውነት ዳኛ ነው፥***
***ኃይለኛም ታጋሽም ነው፥***
***ሁልጊዜም አይቈጣም።***

**7:6-11** መዝሙረኛው ያህዌን ይጠራል፣ ለእሱ ብሎ እንዲሠራ።

1. ተነሥ – ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ ተተኳሪ (መዝ. 3:7 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)። ይህም ግሥ ሊል የሚችለው
   ሀ. ተነሥተህ አድርግ፣ ለእኛ ብለህ ዳኛ/ተዋጊ
   ለ. ንቃ "አትኩሮት ስጥ እና አድርግ" በሚል ስሜት (መዝ. 44:23)
2. ተነሥ – ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724፣ *ኒፋል* ተተኳሪ
3. ተነሣባቸው – ቢዲቢ 734፣ ኬቢ 802፣ ተተኳሪ፣ መዝ. 35:23፤ 44:23፤ 59:4
4. ተመለስ – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ ተተኳሪ (ወይም "ኑር፣" በሚል የሚረዱት፣ ቢዲቢ 442፣ መዝ. 23:6)
5. ደግፈኝ – ቢዲቢ 1047፣ ኬቢ 1622፣ ተተኳሪ፣ መዝ. 26:1፤ 35:24፤ 43:1

ያህዌ ጥሪ ተደርጎለታል፣ በቁጣው እንዲነሣ፣ በኃጢአት ላይ፣ በፍርድ ራሱን እንዲገልጽ። ይህ አስተሳሰብ ቁ. 7 ላይ ተጠቃሏል። ዕብራይስጥ አስቸጋሪ ነው።

**ጄፒኤስኦኤ** "የአሕዛብ ጉባኤ በፊትህ ይሰብሰብ፣ በእነርሱም ላይ በከፍታ ተመለስ"

***ኢኢመቅ*** "የአሕዛብ ጉባኤ በዙሪያህ ይሰብሰብ፤ በእርሱም ላይ በከፍታ ተመለስ"

ጥያቄው " 'አሕዛብ' በዚህ የፍትሕ ዐውደ-ጽሑፍ ለአንድ ግለሰብ ይገጥማሉ?" የሚል ነው። ይህ መዝሙር ፍትሕን የሚሻው

1. በግል ጠላቶቹ ላይ ነው (ቁ. 6፣8)
2. በጣኦት አምላኪ ሕዝቦች (አብድ. ቁ. 5)

"እግዚአብሔር በአሕዛብ ይፈርዳል" የሚለው ቁጥር ቁጥር 8 ላይ የሚጀምረው ሐቅ ለአማራጭ ቁ. 2 ዋጋ ይሰጣል፣ ነገር ግን በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ አስገራሚ ነው።

**7:8 "እንደ ጽድቄ"** ይህ ሐረግ መተርጎም የሚኖርበት በመዝ. 7፡3-5 አኳያ ነው። መዝሙረኛው ኃጢአት-የለሽ ነኝ እያለ አይደለም፣ ነገር ግን እንዳደረገ የተከሰሰበትን አለማድረጉን ለመግለጽ ነው!

ቁጥር 9፣ 17 የያህዌ ጽድቅ የተረጋገጠበትን ተገንዘቡ። መዝሙረኛው ቀኑን ይናፍቃል፣ እግዚአብሔር ሁሉንም ነገር ቀና የሚያደርግበትን፣ የሰዎችን ሁሉ እውነተኛ ሐሳብና ድርጊት የሚገልጥበትን። መጽሐፍ ቅዱስ ግልጽ ያደርጋል፣ ይህ ሥጋዊ ዓለም የተፈጠረው እና የተያዘው በሞራላዊው/ሥነ-ምግባራዊው አምላክ እንደሆነ። እያንዳንዱ በአምሳሉ የተፈጠረ ሰው ለእርሱ ምላሽ ይሰጣል፣ ለሕይወት ስጦታው/መጋቢነቱ (ማቴ. 25:31-46፤ ራዕ. 20:11-15)!

◘ **"የዋህነት"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 1070) ፍችው "ንጽሕና፣" "ያለ ነውር" ነው (መዝ. 25:21፤ 26:1፣11፤ 41:12፤ ምሳ. 2:7፤ 10:9፤ 19:1፤ 20:7፤ 28:6)። እሱም ኃጢአት የለሽነትን የሚያስረግጥ አይደለም፣ ነገር ግን ንጹሕ ሐሳብን/የውስጥ ስሜትን/ልብን የሚያመለክት እንጂ (ዝከ. ቁ. 10b)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 18:20-24 ላይ።

**7፡9 "የኃጥአን ክፋት"** ይህ የሚያመለክተው መዝሙረኛውን የሚከሱትን መዝ. 7፡3-5 ላይ ያለውን ነውን ወይስ ሁሉንም ሰዎች/ሕዝቦች (መዝሙር 2)?

መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይጣራል፣ ክፉን ያበቃ ዘንድ (ቢዲቢ 170፣ ኬቢ 197፣ ያልተጠናቀቀ፣ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ) እና የሚያጸና (ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 464፣ *ፖለል* ያልተጠናቀቀ) ጽድቅን (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡5 ላይ)።

◘ **"እግዚአብሔር ልቡናንና ኵላሊትን ይመረምራል።"** ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (መዝ. 11:4-5፤ 17:3፤ 26:2፤ 66:10፤ 139:23፤ ኤር. 11:20፤ 17:10፤ 20:12)። እግዚአብሔር የልብን ሐሳብ ያውቃል (ቢዲቢ 480፣ ኩላሊት፤ ውስጣዊ ብልቶች እንደ ስሜትና ሞራል ባሕርያት መቀመጫ ይታያሉ)።

**7፡10-11** ለታማኝ ተከታይ ያህዌ ጋሻው ነው (መዝ. 3፡3 ላይ ማስታወሻ ተመልከት)፣ ነገር ግን ለእምነት-የለሽ ተከታይ እሱ "ጻድቅ ፈራጅ" ነው (መዝ. 96፡13)።

**7፡11 "ቁጣ"** ግሡ (ቢዲቢ 276፣ ኬቢ 277፣ አንቀጽ) መዝሙር ላይ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው። ምሳሌ ላይ ብዙ ጊዜ ይገኛል (መዝ. 22:14፤ 24:24፤ 25:23)።

ግሡ የሚገልጸው የያህዌን (ሁለቱም *ኤሎሂም* እና *ኤል* በዚህ ቁጥር ላይ ለመለኮት ጥቅም ላይ ውለዋል) ቀጣይነት ባለው መልኩ ኃጢአትን መቃወሙን ነው። ይህ እሱ እንዲሆን የፈለገው/እንዲሆን የፈጠረው ዓለም አይደለም። ዘፍጥረት 3 አስከፊ ተጽዕኖ አሳድሯል

1. በእግዚአብሔር ላይ (ሆሴዕ 11፡1-4፣ 8-9)
2. በሰዎች ላይ (ሮሜ. 3፡10-18፣23)
3. ሥጋዊ ፍጥረት ላይ (ሮሜ. 8፡18-23)

ኃጢአት ጊዜ እና ዘላለማዊነት ላይ ተጽዕኖውን አሳርፏል!

***መዝሙር* ፡ 7፡12-16**

**[12]ባትመለሱ ግን ሰይፉን ይስላል፥**

**ቀስቱን ገተረ አዘጋጀም**

**[13]የሞት መሣርያንም አዘጋጀበት፥**
**ፍላጻዎቹንም የሚቃጠሉ አደረገ።**
**[14]እነሆ፥ በዓመፃ ተጨነቀ**
**ጉዳትን ፀነሰ ኃጢአትንም ወለደ።**
**[15]ጕድጓድን ማሰ ቈፈረም።**
**ባደረገውም ጕድጓድ ይወድቃል።**
**[16]ጉዳቱ በራሱ ይመለሳል፥**
**ዓመፃውም በአናቱ ላይ ትወርዳለች።**

**7:12 "ባትመለሱ ግን"** ሁኔታዊውን ኪዳን አስተውል። ደግሞም ንስሐ፣ እንደ እምነት፣ የሕይወት ዘመን ሁሉ መሆኑን ተገንዘብ! ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡- ንስሃ መግባት በብሉይ ኪዳን

ይህ ሃሳብ ምንም እንኳን ወሳኝ ቢሆንም እንዲህነውብሎ ለመፈረጅ ግን በጣም አዳጋች ነው፡፡ ብዙዎቻችን ያለን ትርጓሜ ካደረግንበት የእምነት ተቋም ጋር እናያይዘዋለን፡፡ ሆኖም ግንየ "ተቀመጠው" የመጽሐፍ ቅዱሳዊው ትምህርት ትርጓሜ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ባሉ ብዙ የእብራዊያን

(ግሪክ) ቃላትየ"ተቀመጠውን" ትርጉም በማያመለክት መልኩ ተጽዕኖ አድርገውበታል፡፡

የእብራዊያኑ ቃላቶች በዋናነት ሁለት ናቸው፡፡

1*nhm* (BDB 636፤KB 688)

2*swb* (BDB 996፤KB 1427)

የመጀመሪያው *nhm* ፤ከምንጩ ስናየው በተለያየ መልኩ የሚገለጽ በጥልቅ መተንፈስ የሚል ትርጉም የሚሰጥ ይመስላል፡፡

1. "እረፍት" ወይም "ድሎት" (ለምሳሌዘፍ5:29፣ 24:67፣ 27:42፣ 37:35፣ 38:12፣ 50:12፣ በተደጋጋሚ በስሞች ላይ ይገለጻል ፤ዝ.ከ. 2ኛ15:14፣ 1ኛዜና4:19፣ ነህ 1:1፣ 7:7፣ ናሆ 1:1)

2"መጸጸት" (ለምሳሌዘፍ6:6፣7)

3"ሃሳብን መለወጥ" (ለምሳሌዘጸ13:17፣ 32:12፣14፣ ዘኁ23:19)

4"ርህራሄ" (ለምሳሌዘዳ32:36)

ከላይ መረዳት እንደሚቻለው ሁሉም ጥልቅ ስሜትን ያመለክታሉ! ዋናው ነጥብ ይህ ነው፤ ወደ ተግባር የሚለወጥ ጥልቅ ስሜት፡፡ ይህ የተግባር ለውጥ በተደጋጋሚ ጊዜ ወደ ሌሎች ሰዎች የሚጠቁም ቢሆንም፤ር ግን ወደ እግዚአብሔርም ያመለክታል፡፡
ይህ ወደ እግዚአብሔር የተደረገ የአመለካከት እና የምግባር መታደስ ነው ቃሉን የመጽሐፍ ቅዱስዊ ትምህርት ፋይዳ እንዲኖረው ያደረገው፡፡እዚህ ላይ ግን ትልቅ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡ እግዚአብሔርም "አዘነ" ይባላል (ዝ.ከ. ዘፍ6:6፣7፤ ዘፀ32:14፤ መሳ2:18፤ 1ኛሳሙ15:11፣35፤ መዝ106:45)፤ ር ግን ይህ ከመጸጸት ወይም ከኃጥያት የመጣ አይደለም፡፡ ይልቁንም ይህ የእግዚአብሔር ትልቅ ርህራሄ እና ጥበቃን የሚያሳይ ነው(ዝ.ከ. ዘኁ23:19፣ 1ኛሳሙ15:29፣ መዝ110:4፣ ኤር4:27-28፣ ሕዝ24:14)፡፡ ኃጥያተኛው ከልቡ ቢጸጸት እና ከተግባሩም እራሱን አጽድቶ ወደ እግዚአብሔር ከተመለሰ የአመጻ እና የኃጥያተኝነት ቅጣት ይቀራል፡፡
ይህ ቃል ሰፋ ያለ የቋንቋ ትርጓሜ ዘርፍ አለው፡፡ የአንድ ምንባብ ዓውድ የታለመውን ትክክለኛ ትርጓሜ ለመረዳት ትልቅ ሚና አለው፡፡ ሁለተኛው ቃል *swb* ፤ "መመለስ" (ከሆነ ር መመለስ፤ መዞር ፤ ወደ ሆነ ር መዞር ) ማለት ነው፡፡"ንስሃ መግባት" እና "እምነት" (ለምሳሌ፤ማቴ3:2፤ 4:17፤ ማር1:4፣15፤ 2:17፤ ሉቃ3:3፣8፤ 5:32፤ 13:3፣5፤ 15:7፤ 17:3) ሁለቱ ዋነኛ አስፈላጊ የቃል ኪዳኑ ሮች እንደሆኑ እውነት ከሆነ *nhm* የሚያመለክተውየራስን ኃጥያት በጥልቅ ተገንዝቦ ከሱም መመለስ መሆኑን ሲሆን *swb*ከኃጥያት ወደ እግዚአብሔር መመለስን ሊያሳይ ይችላል (ለነዚህ ሁለት መንፈሳዊ ተግባሮች አንዱ ምሳሌ አሞፅ 4:6-10 4:6-11፣ "ወደእኔአልተመለሳችሁም" [አምስት ጊዜ] እና አሞፅ 5:4፣6፣14፣ "እኔንፈልጉእግዚአብሔርንፈልጉመልካሙንእንጂክፉውንአትፈልጉ ")፡፡
የንስሃን ኃይል ጥቅም በተመለከተ የመጀመሪያወና ቀዳሚው ታላቅ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው ዳዊት ከቤርሳቤህን ጋር የፈጸመው ኃጥያት ነው (ዝ.ከ. 2ኛሳሙ12፣ መዝ32፣51)፡፡ በዚህም ምክንያት የተነሳ በዳዊት ፣ በቤተሰቡ እና በእስራኤል ላይ ብዙ ተከታታይ ሮች የተሰቱ ቢሆንም እንኳን ዳዊት ከእግዚአብሔር ጋር ወደ ነበረው ህብረት ተመልሷል! አመጸኛው ምናሴም
እናኳን ንስሃ መግባት እና ይቅርታን ማግኘት ይችላል(ዝ.ከ. 2ኛዜና 33:12-13)፡፡
እነዚህ ሁለት ቃላቶች በመዝ90:13 ውስጥ በተያያዥነት ተጠቅሷል፡፡ ኃጥያተኛነትን መገንዘብ ፣ በእውነተኛ ማንነትምከኃጥያተኝነት መመለስ እና እግዚአብሔርን እና ጽድቁን መፈለግአስፈላጊ ሮች ናቸው (ዝ.ከ. ኢሳ1:16-20)፡፡ንስሃ መግባት አዕምሮአዊ ፣ግላዊ እና ግብረገብአዊ ባህሪያት አሉት፡፡ ከእግዚአብሔር ጋር አዲስ ግንኙነት ለመጀመር እና ለማጠናከር ሁሉም ሁሉም አስፈላጊዎች ናቸው፡፡ ጥልቅ የጸጸት ስሜት ወደ እግዚአብሔር መሰጠት ውስጥ እናለእግዚአብሔር ወደ ማደር ውስጥ ያስገባናል!

## ልዩ ርዕስ፡ መፅናት

የመፅሐፍ ቅዱስን አስተምርሆት ከክርስትና ሕይወት ጋር ለማዛመድና ለመግለፅ አስቸጋሪ ነው ምክንያቱም የምዕራባውያን የአነጋገር ስልት ከመፅሐፍ ቅዱስ ትምህርት ጋር የሚጋጭ ስለሚመስል ነው፡፡ የምዕራባውያን ክርስትና አንድን እውነት የሚመርጥ ሆኖ ነገር ግን ሌላኛውን እውነት የሚሽር ነው፡ በምሳሌ እነመልከት፡-

1. ደህንነት ክርስቶስን ለማመን በመወሰን ወይስ በሕይወት ዘመን ሁሉ በመስጠት ደቂ መዝሙር በመሆን የሚገኝ ሕይወት ነው?
2. ደህንነት የእግዚአብሔር ነፃ ምርጫ ወይስ የሰው የንስሃና የእምነት ፈቃድ ማሳያ ነው?
3. ደህንነትን ካገኙ በኃላ ሊያጡት ይችላሉ? ወይስ በቀጣይነት በትጋት የሚጠበቅ ሕይወት ነው?

በጥንቲቱ ቤተክርስቲያን የትጋት ጥያቄ ዋና ነገር ነበር፡፡ የችገሩ ጅማሬ የተነሣው በአዲስ ኪዳን ምንባቦች መለያየት ነው፡፡

1. የማረጋገጫ ዓውዶች
   ሀ. የኢየሱስ ዓረፍተ ነገሮች (ዮሐ 6፡37፤10፡28-29)
   ለ. የጳውሉስ ዓረፍተ ነገሮች (ሮማ 8፡35-39፤ ኤፊ 1፡13፤2፡5,8-9፤ ፊሊ 1፡6፤2፡13፤ 2 ተሰሎ 3፡3,2፣ ጢሞ 1፡12፤4፡18)
   ሐ. የጴጥሮስ ዓረፍተ ነገሮች (1ጴጥ 1፡4-5)

2. የመፅናት አስፈላጊነት የሚናገሩ ዓውዶች፡-
   ሀ. የኢየሱስ ዓረፍተ ነገሮች (ማቴ 10፡22፤13፡1-9-24-30 ማርቆ 13፡13፤ዮሐ 8፡31፤15፤4-10፤ራዕ 2፡17,)
   ለ. የጳውሉስ ዓረፍተ ነገሮች (ሮማ 11፡22፤1 ቆሮ 15፡2፤2 ቆሮ 13፡5 ገላ 1፡6፤3፡4፤5፡4፤6፡9፤)ፊሊ. 2፡12፤3፡18-20፤ቆላ 1፡23)
   ሐ. የዩሐንስ ዓረፍተ ነገሮች (1 ዮሐ 2፡6፤ 2 ዮሐ 9)
   መ. የዕብራውያን መፅሐፍ (ዕብ 2፡1፤3፡6,14፤4፡14፤6፡11)
   ሡ. የአባት ዓረፍተ ነገር (ራዕ 21፡7)

መፅሐፍ ቅዱስ የሚያስተምረው "ድነት" የእግዚአብሔር ፍቅር፣ ምህረት እና የፀጋው መገለጫ መሆኑ ለሁሉ መታወቅ አለበት፡፡ ያለ መንፈስ ቅዱስ አነሳሽነት ማንም ሰው ወደ ደህንነት ሊመጣ አይቻለውም (ዮሐ 6፡44,65) የመለኮት ጥሪ ቅድሚ ሲሰጠው የሰው ምላሽ በሁለተኛ ደረጃ የሚቀመጥ ነው፡፡ ሁሉ ሙብቱን እና ሃላፊነቱን ማወቅ ይጠበቅበታል፡፡

ደህንነት ለሁሉ የተቸረ የአምላክ ስጦታ ነው፡፡ የኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀል ላይ መሞት የዓለምን ሃጢያት ለማስወገድ ችሏል ይህም እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ ለመዳኛ ያዘጋጀው የደህንነት በር ነው፡፡

የሚከተሉት መፃህፍቶች በማንበብ ተጨማሪ ግንዛቤ በዚህ ርዕስ ጉዳይ ላይ ይቻላል፡፡

1. dale moody, *The word of Truth*, Eerdmans, 1981 (pp 348-365)
2. Howard marshall, *Kept by the Power of God*, Bethany fellow ship, 1969
3. Robert shank, *Life in the Son*, Westcott, 1961

መፅሐፍ በዚህ ርዕስ ላይ ሁለት ሃሳቦችን ያነጣል፡ (1) ማረጋገጫ አገኘን የሚሉ ነገር ግን የተሳሳተ ኑሮ የሚኖሩ የማስጠንቀቂ ቃል የተነጋገራቸው ነገር ግን የሚያገለግሉ፡፡ (2) በራሰው ሕሞትና አግልግሎት ውስጥ የሚታገሉትን አበረታቱ፡፡ ችግሩ ትክክለኛ ያልሆነ ቡድን ስህተት የሆነ ትምህርት ይቀበላል እንዲሁም በተወሰኑ የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባቦች ብቻ ላይ በመደገፍ የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮን ይገነባሉ፡፡ አንዳንድ ክርስቲያኖች የዋስት መልዕክትን የፈልጋሉ፡፡ አንዳንዶች የማስጠንቀቂያ ደወልን አንተ በየትኛው ቡድን ውስጥ ነህ?

**7፡12-13** ንስሐ በማይገቡ ሰዎች ላይ የእግዚአብሔር ርምጃ (ዘዳ. 32:34-43)
1. ሰይፉን ይስላል (መዝ. 17:13)
2. ቀስቱን ይገትራል (ዘካ. 9:13)
3. የሞት መሣርያዎችንም አዘጋጀበት
4. ፍላጻዎቹንም የሚቃጠሉ አደረገ (መዝ. 38:2)

ይህ ቃል ከጦርነት ጋር ይዛመዳል። ይህም ከቁጥር 7 ጋር ይደጋገፋል፣ አሕዛብን በማመልከት፣ እምነተ-ቢስ እስራኤላውያንን ብቻ ሳይሆን።

**7፡14-16** ሆኖም፣ እነዚህ ቁጥሮች፣ የሚያያዙት ከግለሰባዊ ጋር ነው፣ ከብሔራዊ ጠላቶች ጋር ሳይሆን።

1. እነሆ በዓመጻ ተጨነቀ (ከታች ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)
2. ጉዳትን ጸነሰ (ኢዮብ 15፡35፤ ኢሳ. 59፡4)
3. ኃጢአትንም ወለደ
4. ጉድጓድን ማሰ፣ መዝ. 7፡15ሀ

(እነዚህ የተደባለቁ ዘይቤዎች ይመስላሉ፣ ከመውለድ እና ከማደን)

ነገር ግን የተገላቢጦሹን ተገንዘብ (ምሳ. 26:27፤ 28:10፤ መክ. 10:8)።

1. በቆፈረው ጉድጓድ ወደቀ፣ መዝ. 7:15ለ፤ 57:6
2. ጉዳቱ በራሱ ላይ ይመለሳል፣ መዝ. 7:16ሀ፣ለ

**7:14**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ዓመፃ"** |
| **አየተመት፣ ጀፒኤስአኤ** | **"ከፉ"** |
| **አኢመቅ** | **"ከፉነት"** |
| **የተእመቅ** | **"በደል"** |

ለዚህ ስም የሚገጥም ግሥ የለም (ቢዲቢ 19)። ለዚህ ሥር ተጓዳኝ የለውም፣ በፍች ቋንቋዎች። እሱ የሚገኘው በቅኔአዊ ምንባቦች ላይ ነው፣ መዝሙር፣ ኢዮብ፣ ምሳሌ ላይ።

እሱም "ኃይልን" ወይም "ኃይልን አላግባብ መጠቀምን" ከሚገልጽ ሥር የመጣ ሊሆን ይችላል (ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ. 310)። ይህም በያህዌ ተጠልቷል (መዝ. 5:5፤ 11:5)። እሱም ተገቢ ያልሆነ የኪዳን ጠባይ ሊገልጽ ይችላል

1. በአምልኮ (ኢሳ. 1:13፤ ዘካ. 10:2)
2. በፖለቲካ (ኢሳ. 31:2)
3. በፍርድ-ቤት (ኢሳ. 10:1፤ 29:20)
4. በጦር ሜዳ (መዝ. 56:7)

ይህ ቃል የሚገልጸው በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ላይ በተቃውሞ የተመቻቸ ልብን ነው።

***መዝሙር ፡ 7፡17***

[17]**እግዚአብሔርን እንደ ጽድቁ መጠን አመሰግናለሁ፥**
**ለልዑል እግዚአብሔርም ስም እዘምራለሁ።**

**7፡17 "አመሰግናለሁ... እዘምራለሁ"** እነዚህ ሁለቱም አብረው የሚሄዱ ናቸው (መሐላዎች)።

1. ምስጋና ማቅረብ - ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ሂፍል ያልተጠናቀቀ በተመሳሳይ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ምስጋና መዘመር - ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ተመሳሳይ

ኒዶቲ፣ ቅጽ 2 ገጽ 406፣ ቁ. 3 "የምስጋና መሥዋዕት" ይላል፣ እሱም በቃል መልኩ ምስጋና ማቅረብን የሚያጎዳኝ (ማለትም፣ ዝማሬዎች፣ መዝ. 107:22፤ 116:17፤ ዮናስ 2:9)። የኀዘን ጸሎት ዘወትር ምስጋና ማቅረብንና ምስጋናን ያካትታል (መዝ. 35:18፤ 43:4፤ 54:6፤ 56:12፤ 57:9፤ 69:30፤ 71:22፤ 109:30፤ 140:13፤ 142:7)።

▣ **"የጌታ ስም"** ልዩ ርዕስ መዝ. 5፡11-12 ላይ ተመልከት።

▣ **"ልዑል"** ይህ የዕብራይስጥ ስም፣ *ኤሊዮን* (ቢዲቢ 751 II) በመዝሙር ላይ ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል፣ ለያህዌ መጠሪያ (ዘፍ. 14:19፤ ዘኍ. 24:16፤ ዘዳ. 32:8፤ መዝ. 9:2፤ 18:13፤ 21:7፤ 46:4፤ 47:2፤ እና ሌሎች በርካታ ተጨማሪዎች)። እርሱም የመጣው "ከፍተኛ" ወይም "የላይኛ" ከሚለው ቃል ነው (ቢዲቢ 751 I)። እሱም ከያህዌ ጋር ይያያዛል፣ 47:2 ላይ፣ ይኸውም "በምድር ሁሉ ላይ ታላቅ ንጉሥ" ከሚለው ጋር ትይዩ የሆነ። መዝ. 9:2 እና 92:1 ላይ ያው ሐረግ ተደግሟል፣ መዝ. 7፡17 ላይ ያለው።

ይህ ለከፍተኛው ጣዖት መጠሪያ ነበር፣ በከነአናውያን አምልኮ። ሊሆን የሚችለውም እስራኤል ይሄንን ስም እንደወሰደ ነው (በባቢሎንና ፋርስ አማልክት ስሞች ላይ እንዳደረጉት) የእነርሱ አምላክ እውነተኛው ብቸኛ አምላክ መሆኑን ለማስረገጫ መንገድ! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት መዝ. 2፡7 ላይ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በ “ያህዌ” እና “ኤሎሂም” መካከል ያለው ሥነ-መለኮታዊ ልዩነት ምንድነው?
2. የመዝሙረኛው ጠላቶች እሱን የሚከሱበት በምንድነው፣ ቁጥር 3-4 ላይ?
3. “እግዚአብሔር ልብንና ሐሳብን ይመረምራል” የሚለው ጽሑፍ ምንድነው?
4. የዕብራይስጡ ቃል “ንስሐ” እና የግሪኩ ቃል “ንስሐ” በመካከላቸው ያለውን ልዩነት አብራራ።
5. “የተገላቢጦሽ”ን ጽሑፋዊ ጽንሰ-ሐሳብ አብራራ። እሱስ በመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ አዘውትሮ ለምን ይገኛል?

## መዝሙር 8
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር ክብርና የሰው ክብር<br>ኤምቲ መግቢያ "ለመዘምራን አለቃ፤ በጌት።" የዳዊት መዝሙር" | የእግዚአብሔር ክብር በፍጥረት ላይ | የአምላክን ክብር ማክበሪያ ውዳሴ እና አምላክ ለሰው ልጆች የሰጠው ክብር | የእግዚአብሔር ክብር እና የሰው ክብር | የእግዚአብሔር ስም ኃይል |
| | | | | 8:1ሀ |
| 8:1-2 | 8:1 | 8:1ሀ | 8:1-2 | 8:1ለ-2 |
| | | 8:1b-2 | | |
| | 8:2 | | | 8:3-4 |
| 8:3-8 | 8:3-5 | 8:3-4 | 8:3-4 | 8:5-6 |
| | 8:6-8 | 8:5-8 | 8:5-8 | 8:7-8 |
| | | | | 8:9 |
| 8:9 | 8:9 | 8:9 | 8:9 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መኳዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 8፡1-2**
**1አቤቱ ጌታችን፥**
**ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመሰገነ፥**
**ምስጋናህ በሰማዮች ላይ ከፍ ከፍ ብሎአልና።**
**2ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች አፍ ምስጋናን አዘጋጀህ**
**ስለ ጠላትህ፥**
**ጠላትንና ቂመኛን ለማጥፋት።**

**8፡1 "አቤቱ ጌታችን"** ይህ ድብልቅ ነው
1. ያህዌ - የኪዳን ስም (ቢዲቢ 217) የእግዚአብሔር (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡1 ላይ)
2. አዶን - ቃሉ (ቢዲቢ 10) ፍችው "ባለቤት፣" "ባል፣" "ጌታ፣" ወይም "ገዥ" ነው። እዚህ የብዙ ቁጥር ነው። በመዝሙር ቀሪዎቹ ሌሎች ቦታዎች ላይ ይህ መጠሪያ ጥቅም ላይ የዋለው በነጠላ ቁጥር ነው (መዝ. 45:12፤ 57:5፤ 105:21፤ 110:1፤ 114:7፣ ከ136:3 በቀር፣ እዚያም "የጌቶች ጌታ" የሚለው አወቃቀር ጥቅም ላይ የዋለበት። እንግዲያውስ፣ ይህ፣ "የግርማውን ብዙነት" ምሳሌ የሚያሳይ መሆን አለበት።

እነርሱ እዚህጋ አንድ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት ለአንድ አምላክ ነው፣ ነገር ግን መዝ. 110፡1 ላይ በተናጠል ነው ጥቅም ላይ የዋሉት፣ ለያህዌና ለመሢሑ (ማቴ. 22:44፤ ማርቆስ 12:36፤ ሉቃስ 20:42፣43፤ ሐዋ. 2:34፣35፤ ዕብ. 1:13)።

ደግሞም በእንግሊዝኛ ትርጉሞች ሁለቱ ቃላት የሚገለጹት በትልልቆች ፊደላት ነው።

ያህዌ = ጌታ

አዶን = ጌታ

▣

**አአመመቅ፣ አየተመት፣**

**አኢመቅ፣ ጀፒኤስኦኤ** **"ግርማዊ"**

**አኪጀት** **"ግሩም"**

**አእቅ** **"ታላቅነት"**

**የተእመቅ** **"ክብራዊ"**

**አእት መጽሐፍ ቅዱስ** **"አስገራሚ"**

ይህ የዕብራይስጥ ቅጽል (ቢዲቢ 12) ጥቅም ላይ የዋለው ለነገሮች፣ ለሰዎች፣ እና ለእግዚአብሔር ነው። ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ ሲውል፣ የእርሱን ሊደረስ የማይችል ሉዓላዊነት ለመግለጽ ለመሞከር ነው (መዝ. 76:4፤ 93:4)።

የስሙ መልክ (ግሥ የለውም) በመደበኝነት ጥቅም ላይ የሚውለው ለአለባበስ ነው።

1. የዔሳው ፀጉር እንደ ፀጉራም መጎናጸፊያ — ዘፍ. 25፡25
2. ውድ የሆነ ካባ፣ ከኢያሪኮ በአካን የተሰረቀ — ኢያ. 7፡21፣24
3. የኤልያስ መጎናጸፊያ (የያህዌ ኃይል ሰጭነት ተምሳሌት) – 1 ነገ. 19:13፣19፤ 2 ነገ. 2:8፣13፣14
4. የነቢዩ ፀጉራማ መጎናጸፊያ (የትንቢታዊ ሥልጣኑ ተምሳሌት) — ዘካ. 13፡4

እሱም ደግሞ መሆን የሚችለው

1. ክብር — ዘካ. 11፡3
2. የተከበረ — ሕዝ. 17፡8

ይህ ሐረግ በባለቤትነት የተያያዘ ይሆናል (በፍጥረት ላይ የእግዚአብሔር ስፍራ) እንዲሁም ስም "ግርማዊ" (መጎናጸፊያ) የኢሳይያስ 6፡1-4።

▣ **"ስም"** ይህ የሚቆመው ለያህዌ ለራሱ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ስም፣ መዝ. 5፡11-12 ላይ።

▣ **"በምድር ሁሉ"** ይህ የሚያመለክተው አጠቃላዩን ፍጥረት ነው (መዝሙር 104፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 1፡2 ላይ)። ያህዌ ብቻ ነው እውነተኛው ብቸኛ ፈጣሪ፣ ተቤዢ አምላክ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት መዝ. 2፡7 ላይ)።

▣ **"ምስጋናህ በሰማዮች ላይ ከፍ ከፍ ብሎአልና።"** በዕብራይስጥ ጽሑፍ በዚህ ሐረግ ላይ በርካታ ጉዳዮች አሉ።

1. ኤምቲ ተተኳሪ አለው፣ "ሰጠ" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ ተተኳሪ)፣ "ግርማህ ከሰማያት በላይ ነው" (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማያት፣ መዝ.2፡4 ላይ)።
2. የዩቢኤስ ጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 169፣ NIV (አዓት) ተመልከት) ወደ አልተወሰነ ተመሳሳይ ግሥ ይቀይረዋል፣ "ግርማህን ከሰማያት በላይ ከፍ አደረግህ" (ዩቢኤስ ይሄንን ለውጥ "መ" ደረጃ ይሰጠዋል፣ ማለትም፣ "እጅግ አጠራጣሪ")።
3. አእት መጽሐፍ ቅዱስ በተጠናቀቀ ወይም ባልተጠናቀቀ መልክ ይወስደዋል፣ "ግርማህን በሰማያት በላይ ያኖርክ" (ገጽ 857)።
4. መልነቅ መጽሐፍ ቅዱስ (ቅጽ 16፣ ገጽ 45) የሚወስደው "ግርማዊነትህን ከሰማያት በላይ አመልካለሁ" በሚል ነው፣ ግሡን ከዩጋሪት አጠቃቀም ጋር በማዛመድ።
5. ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ በመዝሙር ላይ (ገጽ 78-79፣ አርኢቢ) ዳግም ድምጸት ይሰጠዋል፣ "መንገር" ወይም "ማመስገን፣" በሚል፣ "ክብሩ ከሰማያት በላይ የተነገረ/የተመሰገነ" (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማያት፣ መዝ. 2፡4 ላይ)።

ለግላዊ ማስታወሻ ያህል፣ ይሄንን መዝሙር እና "የስምህ ግርማ እና ክብር" የሚለውን ዝማሬ እወዳለሁ። የእግዚአብሔርን መገኘት ባስደናቂ መንገድ ይሰማኛል፣ ይሄንን መልእክት ሳስብ፣ የአምላካችንን ሊደረስበት የማይቻል አስደናቂነት። አካዳሚያዊ ጉዳዮች ከዚህ አምልኳዊ መልእክት እንዲወስዱኝ አልሻም። ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ፣ እውነት መሆን እሻለሁ፣ ለተመስጧዊው ደራሲ መልእክት! የእግዚአብሔር መንፈስ ይርዳን፣ እሱን እንድናውቀው፣ እሱን እንድናውጀው፣ በእርሱ መገኘት ብርሃን እንድንኖር!

▣ **"ከሰማያት ከፍ ከፍ ብሎ"** ይህንን በበርካታ መንገዶች መረዳት ይቻላል።

1. ሙሉው ቁጥር የፍጥረታትን አምላክ ነው የሚያመሰግነው
2. የእግዚአብሔር ምስጋና እስከ ሰማያት ከፍታ ይደርሳል
3. ፍጥረት የፈጣሪውን ክብር/ግርማ ይናገራል/ይገልጻል (ማለትም፣ የሌሊት ሰማይ፣ መዝ. 8፡3)

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ሰማይ" እና "ሰማያትና ሦስተኛው ሰማይ" መዝ. 2፡4 ላይ።

**8፡2 "ከሕፃናትና ከሚጠቡ ልጆች"** ይህ ግነታዊ ዘይቤ መሆኑ ግልጽ ነው። እነዚህ ሕፃናት መናገር አይችሉም፣ ቢሆንም የእነርሱ መገኘት ብቻ የእግዚአብሔርንና የፍጥረቱን ክብርና ግርማ ያሳያል። ይህ ተፈጥሯዊ መገለጥ ነው፣ የመዝ. 19፡1-6። በእነዚህ የፍጥረት ነገሮች በኩል እግዚአብሔር ይታወቃል (ሮሜ. 1፡19-20፤ 2፡14-16)።

ይህ ቁጥር ከLXX በኢየሱስ ለፈሪሳውያን ተጠቅሷል፣ ወደ ኢየሩሳሌም "በድል መግባቱን" ለሚመለከቱት፣ ማቴ. 21፡16 ላይ።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ ጀፒኤስአኤ** | ***"ኃይልን ታጥቀሃል"*** |
| **አኪጀት** | ***"ኃይል አድርገሃል"*** |
| **አየተመት፣ የተእመቅ** | ***"መከላከያውን መሥርተሃል"*** |
| **አኢመቅ** | ***"ምሽግ አበጀህለት"*** |

*ግሡ* (ቢዲቢ 413፣ ኬቢ 417፣ *ፓይል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 89፡11፣ የተጠናቀቀ) ፍችው "*መመሥረት*" ነው (1 ዜና. 9፡22) ወይም "*የተመሠረተ*" (ኢያ. 6፡26፤ 1 ነገ. 16፡34፤ ዕዝራ 3፡10፤ ኢሳ. 14፡32፤ 28፡16)።

"*ኃይል*" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 738) መደበኛ ፍችው "ብርታት" ነው፣ ነገር ግን በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ እሱ የሚያመለክተው "የመከላከያ ምሽግን" ነው።

የቃላት ጨዋታ አለ "በሚጠቡ ልጆች" (ቢዲቢ 413) እና "*መመሥረት*" መካከል (ቢዲቢ 413)።

ያህዌ፣ ፈጣሪ በሰማያት እና በትንንሾች ይገለጣል። ፍጥረት ሁሉ የእርሱን መገኘትና ተግባር ይገልጻል!

በዚህ ቁጥር ፍች ላይ ርግጠኝነት የለም፣ ነገር ግን ትንንሾቹ የእግዚአብሔርን ክብር የሚገልጹት በጥቃት ሥር ናቸው፣ እግዚአብሔርም እነርሱን ይከላከላል ይጠብቃቸዋልም፣ እውነቱን ለሚገልጹት ሁሉ እንደሚያደርገው!

**8፡2ለ** ክፉ ባላንጣዎችን የሚገልጹትን ቦዝ አንቀጾች አስተውሉ።

1. ተቃዋሚዎች – ቢዲቢ 865 II፣ ኬቢ 1058፣ ቦዝ አንቀጽ
2. ጠላት – ቢዲቢ 33፣ ኬቢ 38፣ ቦዝ አንቀጽ
3. በቀለኛ – ቢዲቢ 667፣ ኬቢ 721፣ *Hithpael* ቦዝ አንቀጽ

የመዝሙረኛው ጠላት ስሞች ላይ ሙሉውን ማስታወሻ መዝ. 1፡5 እና 5፡10 ላይ ተመልከት።

***መዝሙር ፡ 8፡3-8***

***3የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ፥***
***ጨረቃንና ከዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን፥***
***4ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው?***
***ትጐበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?***
***5ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው***
***በክብርና በምስጋና ዘውድ ከለልኸው።***
***6በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው***
***ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት፥***
***7በጎችንም ላሞችንም ሁሉ***
***ደግሞም የምድረ በዳውን እንስሶች፥***
***8የሰማይንም ወፎች የባሕርንም ዓሦች፥***
***በባሕር መንገድ የሚሄደውንም ሁሉ።***

**8፡3** ይህ ቁጥር የሚገልጸው የሰዎችን መደነቅ ነው፣ የሌሊት ሰማይን ሲመለከቱ። ለብዙዎች ጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ለነበሩ ይህ የባዕድ አምልኮና የፍርሃት ምንጭ ነው። ለእስራኤላውያን ግን የያህዌ መግለጫ ነበር (ዘፍ. 1፡14-19)።

"እወጃ" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 464፣ *ፖለል* የተጠናቀቀ) ጥቅም ላይ የዋለው ለእግዚአብሔር ፍጥረት ነው፣ መዝ. 24፡2፤ 119፡90 ላይ። ቀጣዩ ቁጥር የሚያተኩረው እግዚአብሔር ሰዎችን መፍጠሩ ላይ ነው (ዘዳ. 32፡6)። ፍጥረት፣ ውብ ፍጥረት ዓላማ አለው — የእግዚአብሔር መረማመጃ እና ለሰው ልጆች ኅብረት (ሙሉውን ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 2፡8 ላይ)። በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም ነገር በዘፍጥረት 3 እና ራዕይ 20 መካከል ያለው እግዚአብሔር በዔድን ገነት የጠፋውን ኅብረት ሲመልስ ነው። ዘፍጥረት 1-2 እና ራዕይ 21-22 ትይዩ የሆኑት በአጋጣሚ አይደለም!

▣ **"የእጆችህን ሥራ"** ይህ ሰዋዊ ዘይቤ ቋንቋ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 2፡4-6 ላይ።

እንድታነቡ እመክራለው፣ የጆን ዋልተን የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አስተሳሰብና ብኪ፣ ምዕራፍ 7፣ "ኮስሚክ ጂኦግራፊ" ገጽ 165-178፣ ዘመናዊውን አንባቢ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ርዕዮተ ዓለምን ማስተዋወቂያ መንገድ፣ ከእኛ እጅግ የሚለየውን!

ፀሐይንና ጨረቃን ማምለክ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) የተለመደ ነበር። ዘፍጥረት 1 የባቢሎናውያንን የከዋክብት አምልኮ ይቃረናል፣ የግብፅ መቅሠፍት የግብፅን ጣዖታት ባሕርይ እንደሚቃረን።

እግዚአብሔር ሰማያዊ አካላትን ፈጥሯል (ዘፍ. 1፡14-19) ይቆጣጠራቸዋልም።

## ልዩ ርዕስ፡ የጨረቃ አምልኮ

የጨረቃ አምልኮ በጣም በሰፋት የተሰራጨ የጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ አፈታሪክ ነው፣ ከሱመር የተጀመረ (የመጀመሪያው የታወቀ ሥልጣኔ)። አፈታሪኩ ሁለቱንም፣ ወንድና ሴት አፈታሪካዊ ገጽታ አለው። በዋነኛነት የጨረቃ ጣዖት የመጣው በአዝመራዋ ጣዖት መደፈር ነው፣ ኒንሊል በኢንሊል፣ የሰማይ ጣዖት። ኢንሊል ከጣኦታት ውጪ ተጣለ እንዲሁም በሥራው ድርጊት ተኮንኖ ወደ ምድር ውስጥ ተደረገ፣

ነገር ግን ኒንሊል ማርገዟን ስታውቅ ተገናኘችው። ልጁም፣ ሲን (ወይም ዚን)፣ በየምሽቱ ወደ ሰማይ ይወጣ ዘንድ ተፈቀደለት።

የጨረቃ አምልኮ በተለያዩ ምዕራፎች ተከፍሏል፡

1. አዲስ ጨረቃ - አሲምባባር
2. ግማሽ ጨረቃ - ሲን
3. ሙሉ ጨረቃ - ናና (ሱሜሪያዊ "ብርሃን መስጠት" ከኢን-ሱ፣ "የጥበብ ጌታ")

እነዚህ ስሞች በመሠረቱ የሚሉት "ጥበበኛ ጌታ" (ማለትም፣ ሱን) ወይም "ብርሃን ሰጪ" (ናና)፣ በዑር በከለዳውያን የሚመለክ ነው።

ከተማው ራሱ ዘወትር የሚጠራው የናናር ከተማ ተብሎ ነው። የመራቢያ ጥንዶች በዚጉራተስ ይመለኩ ነበር (ትላልቅ ፒራሚዶች፣ ጠፍጣፋ አናት ያላቸው) በከተማው የተተከሉ። የፀሐይ አምላክ (ሻማሽ) የጥንዶቹ የበኩር ልጅ ነበር በኋላም ኢሪሽኪጋል (የሥረኛው ዓለም ንግሥት) እና ናና (የመንግሥተ -ሰማይ/ሰማይ ንግሥት)።

አምልኮው እስከ ANE (ጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ድረስ ተሰራጭቶ ነበር፣ ነገር ግን ዋነኞቹ የማምለኪያ ማዕከላት የነበሩት

1. ዑር
2. ካራን
3. ቴማ
4. ከነዓን
5. መካ

በመሠረቱ ይህ አፈታሪክ፣ መራባትን ተጋንኖ ከአስትራል አምልኮት ጋር ያደባልቃል።

ብሉይ ኪዳን የጣዖት አምልኮን ይጸረራል (ዘዳ. 4:19፤ 17:3፤ II ነገሥ. 21:3፣5፤ 23:5፤ ኤር. 8:2፤ 19:13፤ ሶፎ. 1:5) እና የርቢ አምልኰን (ማለትም፣ በአል እና አሽራህ፣ ዩጋሪት ግጥሞች)። ዕብራውያን፣ ከመነሻቸው ዘላኖች፣ የጨረቃ አምልኮን ለመቃወም በጣም ይጠነቀቁ ነበር፣ ምክንያቱም የጨረቃ አምልኮ በአጠቃላይ በሌሊት የሚጓዙ ዘላን ሕዝቦች ባሕርይ ስለነበር ነው፤ በሌላ መልኩም ፀሐይ ደግሞ በእጅጉን ባጠቃላይ ይመለክ የነበረው በሰፈሩ አራሽ ሕዝቦች ነበር። እየቆየም ዘላኖቹ ሲሰፍሩ ከዚያም የአስትራል አምልኮ በአጠቃላይ ችግር ሆነ።

**8፡4** ተመሳሳይነት ያለውን ትይዩ ተገንዘቡ፣ በሁለቱ የቅኔ ስንኞች መካከል፣ በተለይም "ሰው" (ቢዲቢ 60፣ *ኤኖሽ*፣ መዝ. 9:20፣ ደግሞም መዝ. 103:14 ተገንዘቡ) እናም "የሰው ልጅ" (ቢዲቢ 119 አወቃቀር ቢዲቢ 9፣ "የሰው ልጅ፣" "*ቤን አዳም*፣" መዝ. 144:3)።

የመጀመሪያው ቃል፣*ኤኖሽ*፣ ሁለት ፍችዎች አሉት።

1. ቢዲቢ 60 I – ደካማ፣ ሕመምተኛ፣ ተሰባሪ (ከዕብራይስጡ ግሥ፤ *ኒፋል*፣ 2 ሳሙ. 12:15፤ ተገብሮ፣ ኢሳ. 17:11፤ ኤር. 15:18፤ 17:9)
2. ቢዲቢ 60 II – የሰው ልጅ እዚህጋ ጥቅም ላይ የዋለው ደካማ በማይለው ፍችው ነው፣ ፍጹም ተቃራኒ

ሁለተኛው ቃል/ሐረግ "የሰው ልጅ" የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ለሰው ልጅ (ማለትም፣ መዝ. 146:3፤ ሕዝ. 2:1)። ያህዌ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፣ ለልዕለ ፍጥረቱ፣ በአምሳሉ ለተሠራው (ዘፍ. 1:26-27)፣ ለኅብረት (ዘፍ. 3:8)። ሰዎች ዋነኛ ፍጥረት ናቸው፣ በተለየ መልኩ ከእግዚአብሔር ጋር የሚዛመዱ። እኛ የዚህ ፍጥረት አካል ነን፣ እናም ከሥጋዊው በላይ! አንዴ ስንፈጠር፣ ዘላለማዊ ነን፣ መንፈሳዊ ፍጥረታት።

ሰዎች በልዕለ መንፈሳዊ ተራ ላይ ናቸው፣ ከመላእክት ይልቅ። ይህ የሚያስቅ ድምፀት እንዳለው አውቃለሁ፣ ግን ከእኔ ጋር አስቡ።

1. የትኛውም መልአክ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል እንደተሠራ አልተባለም (ዘፍ. 1፡26-27)
2. ኢየሱስ መላእክት ለመዋጀት አልሞተም (ዕብ. 2፡14-16)
3. አማኞች በመላእክት ይፈርዳሉ (1 ቆሮ. 6፡3)
4. መላእክት የሰው ልጅን የሚያገለግሉ ናቸው (ዕብ. 1፡14)

በሱመር ኋላ ላይ ባቢሎን ሐተታ ተፈጥሮ ላይ፣ ሰዎች ጫኚ፣ አስቸጋሪ፣ እና ብኩን ነበሩ (የዘፍጥረት 1-11 መግቢያ ማስታወሻን ተመልከት)፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ግን ፍጹም ተቃራኒው ነው። እነርሱ የያህዌ ፍጥረት ድርጊት አትኩሮት ናቸው።

■

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ታስበው ዘንድ"** |
| **አኪጀት፣ አየተመት፣** | |
| **ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ፣** | |
| **LXX** | **"ታስበው ዘንድ"** |
| **አእቅ** | **"ታስባቸው ዘንድ"** |
| **አኢመቅ** | **"ስለ እነርሱ ሐሳብ ታደርግ ዘንድ"** |

*ግሡ* (ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ ያልተጠናቀቀ) ፍችውም "ማሰብ፣" "በበጎነት ማሰብ" በሚል መልኩ (መዝ. 9:12፤ 78:39፤ 98:3፤ 103:14፤ 105:8፣42፤ 106:45፤ 111:5፤ 115:12፤ 136:23)። በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ ዘወትር፣ እግዚአብሔር የሰዎችን ኃጢአት

"እንዲረሳ" ሲነገር፣ እንዲሁም ሰዎች እግዚአብሔርን "እንዲያስቡ" ይነገራል፣ ነገር ግን እዚህ ዘማሪው የሚደነቀው በፍጥረት ስፋትና ውበት ነው፣ እንዲሁም ፈጣሪ በዚች አንዲት ዓለም ላይ ላለ የተለየ ፍጥረቱ ጊዜና ሐሳብ እንዳለው የሚያሳይ አስተሳሰብ ነው! ነገር ግን፣ ይህ እውቀታዊ/ሥነ-መለኮታዊ ጥያቄ ነው፣ አይደለምን (ማለትም፣ ተፈጥሯዊነት በተቃርኖ ባለ ዓላማ ፈጣሪ)?

**8:5** የሰዎች ክብርና ጠቀሜታ በዚህ ቁጥር ላይ በግልጽ ይታያል። "ተሥርተናል" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 341፣ ኬቢ 338፣ ያልተጠናቀቀ፣ መክ. 4:8) ፍችውም "እንዲያጣ መደረግ" ወይም "ዝቅተኛ ማድረግ" ለራሱ ለእግዚአብሔር (ኤሎሂም)። LXX ይህንን የሚተረጉመው እንደ "መልአክ" ነው (ዕብ. 2:7)፣ ነገር ግን የመዝሙር 8 ዐውደ-ጽሑፍ "እግዚአብሔር" ይላል፣ ይህ መዝሙር የእግዚአብሔርን የዘፍጥረት ፍጥረት ስለሚያንጸባርቅ። ደግሞም የብዙ ቁጥሩ "እኛ" ዘፍ. 1:26፤ 3:22፤ 11:7፣ የእግዚአብሔርን ሰማያዊ ጉባኤ ቢያንጸባርቅም (1 ነገ. 22:19-23፤ ኢዮብ 1:6፤ 2:1፤ መዝ. 82:1፣6፤ 86:8፤ 89:6፣8፤ ዳን. 7:10)፣ እና ብሎም፣ በመሪነት ላይ ያሉትን መላእክት ያንጸባርቃል (ዘፍ. 3:5)። ሆኖም፣ ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ "እግዚአብሔር" እጅግ የተሻለ እንደሚሆን አስባለሁ።

*ሔኖሽ/ቤን/አዳም መቀዳጀቱን ተገንዘብ*

1. ክብር — ቢዲቢ 458
2. ግርማ — ቢዲቢ 214

ሰው የእግዚአብሔር ላዕላይ ፍጥረት ነው። እነርሱ የተፈጠሩት ከእግዚአብሔር ጋር ለሚሆን ኅብረት ነው። እነርሱ የሚሠሩት በምድር ላይ እንደ እርሱ ተቆጣጣሪዎች ነው (ዘፍ. 1:28)። ሁሉም ሥጋዊ ፍጥረት እንደ መድረክ ነው፣ እግዚአብሔርና የሰው ልጅ እንዲገናኙ እና እርስ በርሳቸውም እንዲተዋወቁ (ዘፍ. 3:8)።

**8:6-8** *መዝ.* 8:3 በርግጥ የዘፍጥረት ቅኝት እንዳለው ሁሉ፣ እንዲሁ ደግሞ ቁጥር 6 (ዘፍ. 1:28)። ሰዎች የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነበሩ፣ በገነት (እና በአንድምታው ፍጥረት ሁሉ)። ሰዎች ይገዛሉ (ቢዲቢ 605፣ ኬቢ 647፣ ያልተጠናቀቀ)፣ በቁጥጥር ሥር ያደርጋሉ (ቢዲቢ 461፣ ኬቢ 460፣ ተተኳሪ፣ ዘፍ. 1:28)፣ ገዥነት አላቸው (ቢዲቢ 921፣ ኬቢ 1190፣ ተተኳሪ፣ ዘፍ. 1:28) ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት ብቻ! መጋቢዎች ነን!

◘ ***"የእጆችህን ሥራ"*** ይህ የሚያመለክተው ዘፍጥረት 1 ነው (ኢዮብ 14:15፤ መዝ. 92:4፤ 138:8፤ 143:5)፣ እንደ "ጣቶችህ ሥራ" ቁ. 3 ላይ (መዝ. 102:25)። አስገራሚ የሚሆነው ዘፍጥረት 1 ላይ የእግዚአብሔር የፈጠራ ሥራ በንግግር ቃል ነው። የሰው ልጅ ብቻ ነው በተለየ ትኩረት የተሠራው/የተበጀው፣ ዘፍ. 2:7 ላይ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደሰው ሲገለጽ (ሰዋዊነት) መዝ. 2:4-6 ላይ።

**8:7** የእነዚህ ፍጥረታት የፍጥረት ተርታ ዘፍጥረት 1 ላይ ትይዩ ነው። ይህ መዝሙር (እንደ መዝሙር 104) ከዘፍጥረት 1 ቅኝት አኳያ መነበብ ይኖርበታል! ዘፍጥረት 1-2 በመዝሙር ላይ ካሉ፣ ስለ ዘውጋቸው ወይም ጥሬአዊነታቸው መከራከር አይኖርብንም!

***መዝሙር ፡ 8:9***

**9 አቤቱ ጌታችን፥**
**ስምህ በምድር ሁሉ እጅግ ተመሰገነ።**

**8:9** ይህ መዝሙር የሚያበቃው እንዳጀማመሩ ነው (ቁ. 1ለ)። የመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጥና ዋነኛው ገጸ-ባሕርይ እግዚአብሔር ነው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "ሰማያት" እና "ሕፃናቶች" እንዴት ይዛመዳሉ?
2. ያህዌ "ጣቶች" አለውን?
3. ያህዌ ፀሐይና ጨረቃን መፍጠሩ ከሥነ-መለኮት አኳያ ጠቀሜታው ለምንድር ነው?
4. ቁጥር 4ሀ ላይ ያለው "ሰው" ቁጥር 4ለ ላይ ካለው "የሰው ልጅ" ጋር እንዴት ይዛመዳል?
5. ሰው ከመላእክት ወይም ከእግዚአብሔር ጥቂት ያንሳልን? ለምን?

# መዝሙር 9
# የአዲሶቹ ትርጕሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የምስጋና መዝሙር፣ ለእግዚአብሔር ፍርድ<br><br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>"ለመዘምራን አለቃ፤ በሙትላቤን የዳዊት መዝሙር" | ጸሎትና ምስጋና ለጌታ የጽድቅ ፍርድ | ጸሎት ከግል ጠላቶች ለመታደግ<br>(መዝሙር 9-10፣ ሰቆቃ) | ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ፣ ስለ ፍርዱ | እግዚአብሔር ክፉዎችን ይመታል፣ ትሑታንን ይታደጋል (መዝሙር 9-10) መስቀልያ |
| 9:1-2 | | | | |
| | 9:1-2 | 9:1-2 | 9:1-2 | 9:1 (*ሓሌፍ*) |
| | | | | 9:2 |
| 9:3-6 | | | | |
| | 9:3-5 | 9:3-4 | 9:3-4 | 9:3-4 (*ቤት*) |
| | | 9:5-6 | 9:5-6 | 9:5-6 (*ጋሜል*) |
| | 9:6-8 | | | |
| 9:7-10 | | | | |
| | | 9:7-8 | 9:7-8 | 9:7-8 (*ሂ*) |
| | 9:9-10 | 9:9-10 | 9:9-10 | 9:9-10 (*ዋው*) |
| 9:11-16 | | | | |
| | 9:11-12 | 9:11-12 | 9:11-12 | 9:11-12 (*ዛይን*) |
| | 9:13-14 | 9:13-14 | 9:13-14 | 9:13-14 (*ሂት*) |
| | 9:15-16 | 9:15-16 | 9:15-16 | 9:15-16 (*ቴት*) |
| 9:17-20 | | | | |
| | 9:17-18 | 9:17 | 9:17-18 | 9:17 (*ዮድ*) |
| | | | | 9:18 (*ቃፍ*) |
| | 9:19-20 | 9:19-20 | 9:19-20 | 9:19-20 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. አዲሱ ኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (አኢመቅ) የሚያስረግጠው መዝሙር 9 እና መዝሙር 10 ላላ ያለ መስቀልያ እንደሚፈጥሩ ነው (ዝከ. LXX)።

ለ. መስቀልያዎች የተለየ ዓይነት ቅኔዎች ናቸው። እያንዳንዱን ፊደል ለማሳካት
1. ያልፎ አልፎ ቃላት ጥቅም ላይ ይውላሉ
2. ያልፎ አልፎ ዓይነት ቃላት ጥቅም ላይ ይውላሉ
3. ተፈጥሯዊ ያልሆኑ የቅኔ ስንኞች ይከሰታሉ
4. ያልተለመዱ ዘይቤዎችና ምሳሌያዊ ቋንቋ ይከሰታሉ
5. የመስተጻምር አጠቃቀም

የጥንቶቹ፣ ፊደላቱ አስማታዊ ጠቀሜታ እንዳላቸው ይሰማቸዋል (ማለትም፣ ካባላ፣ ራስ ሻምራ ጽሑፎች)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

***መዝሙር ፡ 9፡1-2***

**[1]አቤቱ፥ በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፥**
**ተአምራትህንም ሁሉ እነግራለሁ።**
**[2]በአንተ ደስ ይለኛል፥ ሐሤትንም አደርጋለሁ**
**ልዑል ሆይ፥ ለስምህ እዘምራለሁ።**

**9፡1-2** ይህ የመክፈቻ አንጓ አምስት ተጓዳኞች አሉት።
1. ምስጋና አቀርባለሁ — ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ያልተጠናቀቀ፣ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. እናገራለሁ — ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765፣ ተጓዳኝ
3. እደሰታለሁ — ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ ተጓዳኝ
4. ሐሤት አደርጋለሁ — ቢዲቢ 763፣ ኬቢ 836፣ ተጓዳኝ
5. ምስጋና እዘምራለሁ — ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ተጓዳኝ

እነዚህ ሁሉ ከያህዌ ጋር ይዛመዳሉ (ማለትም፣ ልዑሉ)። ምስጋና ማቅረብና ውዳሴ የሰው ልጅ ተግባራት ናቸው። እነዚህ የቅርበት፣ የግል ግንኙነት፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚደረግ የየቀኑ ግንኙነት ምልክቶች ናቸው።

አራቱን "እኔ አደርጋለሁ" ተመልከቱ፣ ቁ. 1-2 ላይ ያሉትን፣ በአምስቱ "አንተ አድርገሃል" ላይ መመሥረታቸውን መዝ. 9፡4-6። ያህዌ አድርጓል! አሁን ደግሞ የእሱ ተከታዮች ሊያመሰግኑት ይችላሉ!

**9፡1 "በልቤ ሁሉ"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጠ ነው፣ ፍጹም ለሆነ መሰጠት መዝሙር 86:12፤ 111:1፤ 138:1፤ 1 ነገ. 8:23፣61፤ 11:4፤ 1 ዜና. 28:9)። ለ "ልብ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 4:7 ላይ።

▣
**አአመመቅ፣ አኢመቅ፣**
**ጀፒኤስአኤ** ***"ተአምራት"***
**አኪጀት** ***"አስደናቂ ሥራዎች"***
**አየተመት፣ የተእመቅ፣**
**LXX** ***"አስደናቂ ሥራዎች"***

ይህ የዕብራይስጥ አወቃቀር ነው (ቢዲቢ 481 እና ቢዲቢ 810፣ ቦዝ አንቀጽ)። ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ አስደናቂ ነገሮች (אלפ)

ይህ ቃል (ቢዲቢ 810) የሚገልጸው የሰው ልጆች በራሳቸው ሊቀዳጁቸው የማይችሏቸውን ድርጊቶች ነው፣ ወይም ይልቁንም ሊያስረዷቸው የማይችሏቸውን ድርጊቶች፣ እነርሱም መደነቅና ፍርሃትን የሚፈጥሩ (ዘፍ. 18:14፤ ኤር. 32:17,27፤ ዘካ. 8:6)።
*ግሥ*
1. ዘጸአት፣ ዘጸ. ዘጸ. 3:20፤ 34:10፤ ሚኪ. 7:15
2. መቅሠፍቶች ዘዳ. 28:59
3. ዮርዳኖስን መሻገር ኢያ. 3:5
4. የእግዚአብሔር ፊተኞቹ ሁነቶች መሳ. 6:13፤ 1 ዜና. 16:9,12,24፤ ነህ. 9:17
5. የሳምሶን ልደት፣ መሳ. 13:19
6. ዳዊት ለዮናታን ያለው ፍቅር፣ 2 ሳሙ. 1:26
7. ዘወትር ኢዮብ ላይ፣ 5:9፤ 9:10፤ 10:16፤ 37:5,14፤ 42:3
8. ሠላሳ ሁለት ጊዜ፣ መዝሙር ላይ
9. የያህዌ ምክር፣ ኢሳ. 28:29
10. የያህዌ ድርጊቶች፣ ኢሳ. 29:14 (ሁለቴ)፤ ኢዩኤል 2:26

ስም

1. ዘጸአት፣ ዘጸ. 15:11፤ መዝ. 77:11,14፤ 78:12
2. ከሙታን ጋር በተያያዘ፣ መዝ. 88:10,12
3. ሰማይ የያህዌን ድርጊት ያመሰግናል፣ መዝ. 89:5
4. የያህዌ ሕግጋት፣ መዝ. 119:129
5. የያህዌ መሢሕ፣ ኢሳ. 9:6
6. የያህዌ ድርጊቶች፣ ኢሳ. 25:1፤ 29:14
7. የፍጻሜ ዘመን ድርጊቶች፣ ዳን. 12:6

እግዚአብሔር በኃይል፣ በሚዋጅ መንገድ ይሠራል፣ ራሱን ለመግለጥ፣ ለልዕለ ፍጡሩ (ለሰው ልጅ)። እሱም እንዲያውቁትና እንዲታመኑበት ይሻል። ድርጊቶቹ መገለጦች ናቸው፣ እነዚያ ድርጊቶች በተመስጦ የተመዘገቡበት፣እና እነዚያ ድርጊቶች ተብራርተው መረዳት የሚቻሉበት። ያህዌ ዓለም እንዲያውቀው ይፈልጋል!

**9፡2 "በአንተ… ለስምህ"** እነዚህ ትይዩ ናቸው። በአምልኮ ላይ ያለውን ግላዊ ነገር ተገንዘብ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ስም መዝ. 5፡11-12 ላይ።

**መዝሙር ፡ 9፡3-6**

**³ጠላቶቼ ወደ ኋላ በተመለሱ ጊዜ፥**
**ይሰናከላሉ ከፊትህም ይጠፋሉ።**
**⁴ፍርዴንና በቀሌን አድርገህልኛልና**
**ጽድቅን እየፈረድህ በዙፋንህ ላይ ተቀመጥህ።**
**⁵አሕዛብን ገሠጽህ፥ ዝንጉዎችንም አጠፋህ፥**
**ስማቸውንም ለዘላለም ደመሰስህ።**
**⁶ጠላቶች በጦር ለዘላለም ጠፉ፥**
**ከተሞቻቸውንም አፈረስህ፥**
**ዝከራቸውም በአንድነት ጠፋ።**

**9፡3-6** ይህ አንጓ ያህዌን ያመሰግናል፣ እንደ ጻድቅ ፈራጅ (መዝ. 9፡4ለ)።
የእርሱ ድርጊቶች በጠላት ላይ መሆናቸውን ተገንዘብ።
1. ጠላቶች ወደ ኋላቸው ተመለሱ፣ ቁ. 3ሀ — ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ ያልተወሰነ አወቃቀር (ማለትም፣ በውጊያ)
2. ጠላቶች ተሰናከሉ፣ ቁ. 3ለ — ቢዲቢ 505፣ ኬቢ 502፣ ያልተጠናቀቀ
3. ጠላቶች ጠፉ፣ ቁ. 3ለ — ቢዲቢ 1፣ ኬቢ 2፣ ያልተጠናቀቀ
4. አሕዛብን ገሥጽክ፣ ቁ. 5ሀ — ቢዲቢ 172፣ ኬቢ 199፣ የተጠናቀቀ (አእት መጽሐፍ ቅዱስ ይህን የሚመለከተው "ለጦርነት ጩኸት" ነው፣ ገጽ 858፣ ቁ. 19)
5. ክፉዎችን አጠፋህ፣ ቁ. 5ሀ፣ — ቢዲቢ 1፣ ኬቢ 2፣ የተጠናቀቀ
6. ስማቸውንም ደመሰስክ፣ ቁ. 5ለ — ቢዲቢ 562፣ ኬቢ 567፣ የተጠናቀቀ (ማለትም፣ በጦርነት ሞቱ)
7. የጠላቶን ከተሞች አፈረስህ፣ ቁ. 6 — ቢዲቢ 684፣ ኬቢ 737፣ የተጠናቀቀ

የያህዌ ባሕርይ ምን እንደሚመስል ተገንዘብ።
1. ፍርዴን አድርገህልኛልና
2. ጽድቅን እየፈረድክ በዙፋንህ ተቀመጥክ
3. መዝ. 9፡7-8 (በቀጣዩ አንጓ ላይ ለአጽንዖት ተደግሟል)

ሊሆን የሚችለው "በጽድቅ ፈራጁ" ያህዌ ነው፣ ለመዝሙረኛው የሚያደርግለት፣ ለኪዳኑ ሕዝብ ንጉሥ በመሆኑ።

**9፡3 "ከፊትህም ይጠፋሉ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 1፣ ኬቢ 2) ቁ. 5፣ 6፣ 18 ላይ መደገሙን ተገንዘቡ። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው
1. ግለሰብ ጠላቶች
2. አሕዛብ
3. የተጎዱት (በአሉታዊ)

እሱ በግልጽ የሚያመለክተው ሥጋዊ ሕይወትን ነው፣ ነገር ግን ደግሞ ዘላለማዊ ሕላዌ ነው (ዝከ. ቁ. 6፣ የዕብራይስጥ ፈሊጥ)። እግዚአብሔርንና ሕዝቡን መቃወም አደገኛ ድርጊት ነው፣ በጊዜያዊም ሆነ በፍጻሜ መዘዞች።

**9፡5 "አሕዛብ"** ተመሳሳይ መልክ ነው፣ ከአንድ ግለሰብ እስከ "አሕዛብ" (መዝ. 9፡17-20)፣ መዝ. 7፡6-7 ላይ ይከሰታል። ብዘዎቹ መዝሙራት በግለሰቦች የተጻፉት በጋራ አምልኮ ላይ የሁሉም ይሆናሉ።

ደግሞም ያህዌ እንደ ፈራጅ የሚገለጽበትን ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 7፡7 ላይ (መዝ. 9፡4-6፣ 7-8)።

▣ **"ስማቸውንም ለዘላለም ደመሰስህ"** "የቋሚ" ፍርድ ጭብጥ እንዴት እንደተደገመ ተገንዘብ (መዝ. 69፡28)።

1. ደመሰስከ፣ ቁ. 5 (የተጠናቀቀ፣ መዝ. 69:28፤ ደግሞም ዘኍ. 5:23፤ ዘዳ. 9:14፤ 25:19፤ 29:20 ተገንዘብ)
2. ለዘላለም፣ ቁ. 5 (ልዩ ርዕስ ከታች ተመልከት: ዘላለም)
3. ለዘላለም አፈረስህ ቁ. 6 (የተጠናቀቀ፣ ኤር. 25:9፤ 49:13)
4. ዝክራቸውም በአንድነት ጠፋ፣ ቁ. 6 (የተጠናቀቀ መዝ. 34:16፤ 109:15)

ቁጥር 5-6 የሚያስታውሰኝ ሚልኪያስ 1 ላይ ያለውን የመክፈቻ ንግግር ነው፣ እዚያም የእስራኤል ሕላዌ በተቃርኖ የሚቀርብበት፣ ከዔዶም አጠቃላይ ፍጻሜ ጋር፣ ለያህዌ የኪዳን ፍቅር እንደ ማስረጃ። የጥንቶቹ የአካባቢው ሕዝቦች ወዴት አሉ? እነርሱ ለታሪክ ጠፍተዋል፣ እስራኤል ሳይሆን!

"ተደመሰሱ" የሚለው ግሥ (ቁ. 1) የሕይወት መጽሐፍን ሊጠቅስ ይችላል።

## ልዩ ርዕስ፡ ዘላለም (ኦላም)

የዕብራይስጡ ስርወ ቃል ‹ mlwu ኦላም› ትርጉም የተረጋገጠ አይደለም፡፡ ቃሉ በተለያዩ አገባቦች በብዙ ቦታ እጥቅም ላይ ውሎአል (በርግጥ ትርጉሙ በአውድ ይወሰናል)፡፡ ከዚህ የሚከተሉት ጥቅሶ ለምሳሌነት የተመረጡ ናቸው፡፡

1. የጥንት ነገሮች
   ሀ. ሕዝቦች፣ ዘፍ.6÷4፤1ኛ ሳሙ.27÷8፤ ኤር.5÷15፤ 28÷8
   ለ. ቦታዎች፣ ኢሳ.58÷12፤61÷፡4
   ሐ. እግዚአብሔር፣ መዝ.93÷2፤ምሳሌ 8÷23፤ ኢሳ.63÷16
   መ. ነገሮች፣ ዘፍ.49÷26፤ኢዮ.22÷15፤መዝ.24÷፡7፣9፤ኢሳ.46÷9
   ሠ. ጊዜ፣ ዘዳ.32÷7፤ኢሳ.51÷9፤63÷9፣11
2. የወደፊት ጊዜ
   ሀ. የሰው ሕይወት፣ ዘፀ.21÷6፤ዘዳ.15÷17፤1ኛ ሳሙ.1÷22፤27÷12
   ለ. ለንጉስ የተደረገ ግነትን፣ 1ኛ ነገ.1÷31፤መዝ.61÷7፤ነህ.2÷3
   ሐ. ቀጣይ ሕልውና
      (1) መሬት፣ መዝ.78÷69፤104÷5፤መክ.1÷4
      (2) ሰማያት፣ መዝ.148÷6
   መ. የእግዚአብሔር ሕልውና
      (1) ዘፍ.21÷33
      (2) ዘፀ.15፡18
      (3) ዘዳ. 32÷40
      (4) መዝ. 93÷2
      (5) ኢሳ.40÷28
      (6) ኤር.10÷10
      (7) ዳን.12÷7
   ሠ. ቃል ኪዳን
      (1) ዘፍ.9÷12፣16፤ 17÷7፣13፣19
      (2) ዘፀ.31÷16
      (3) ዘሌ.24÷8
      (4) ዘሑ. 18÷19
      (5) 2ኛ.ሳሙ.23÷5
      (6) መዝ.105፡÷10
      (7) ኢሳ.24፡÷5፤55÷3፤61÷8
      (8) ኤር.32÷40፤50÷5
   ረ. ከዳዊት ጋር ልዩ ቃል ኪዳን
      (1) 2ኛ ሳሙ 7÷19፣16፣25፣29፤22÷51፤23÷5
      (2) 1ኛ ነገ.2÷33፣45፤9፡
      (3) 2ኛ ዜና 13÷5
      (4) መዝ.18÷50፤89÷4፣28፣36፣37
      (5) ኢሳ.9÷7፤16÷5፤37፡35፤55÷3
   ሰ. የእግዚአብሔር መሲህ
      (1) መዝ.45÷2፤72፡17፤89÷35-36፤110÷4
      (2) ኢሳ.9፡6
   ሸ. የእግዚአብሔር ሕግ
      (1) ዘፀ.29÷28፤30÷21

(2) ዘሌ.6÷18፤22፤7÷34፤10÷15፤24÷9
(3) ዘሑ.18÷8፤11፤19
(4) መዝ.119÷89፤160
(5) ኢሳ.59÷21

ቀ. የእግዚአብሔር ተስፋ ቃል
(1) 2ኛ ሳሙ.7÷13፤16፤25፤22÷51
(2) 1ኛ ነገ. 9÷5
(3) መዝ.18÷50
(4) ኢሳ.40÷8

በ. የአብራሃም ዘሮችና የቃል ኪዳኑ ምድር
(1) ዘፍ.13÷15፤17÷18፤48÷4
(2) ዘፀ.32÷13
(3) 1ኛ ዜና 16÷17

ተ. የቃል ኪዳኑ ግብዣ
(1) ዘፀ.12÷14፤17፤24
(2) ዘሌ.23÷14፤21፤41
(3) ዘሑ.10፡8

ቸ. ዘላለማዊ/ዘላለምነት የዘላለም
(1) 1ኛ ነገ.8÷13
(2) መዝ.61÷7-8፤77÷8፤90፡2፤103÷17፤145÷13
(3) ኢሳ.26÷4፤45÷17
(4) ዳን.9÷24

ኘ. አማኞች ለዘላለም ስለሚያደርጉት ነገር መዝሙር የሚለው
(1) ምስጋና ማቅረብ፣ 30÷12፤79÷13
(2) በሕልውናው ማደር 41÷12፤61÷4፤7
(3) በምህረቱ መታመን 52÷8
(4) እግዚአብሔርን ማመስገን፣ 52÷9
(5) ምስጋናን መዘመር፣ 61÷7፤89÷1
(6) የእርሱን ፍትህ ማወጅ፣ 75÷9
(7) ስሙን ማክበር፣ 86÷12፤145÷2
(8) ስሙን መባረክ፣ 145÷1

3. ያለፈና የሚመጣ ጊዜ (ከዘላለም እስከ ዘላለም)
ሀ. መዝ.41÷13 (ምስጋና ለእግዚአብሔር)
ለ. መዝ.90÷2 (እግዚአብሔር ራሱ)
ሐ. መዝ.103፡17 (የእግዚአብሔር ቸርነት)

የቃሉን ትርጉም ቃሉ ያለበት አውድ እንደሚወስን አትርሳ፡፡ ዘላለማዊ ቃል ኪዳኖችና የተስፋ ቃሎች በሁኔታ ላይ የተመሠረቱ ናቸው (ኤር.7)፡፡ በዘመንህ ስለጊዜ ያለውን አስተሳሰብ ወይም የተቀናጀ የአዲስ ኪዳን ሥነ መለኮት እንደፈሳሽ የሆነው ይህ ቃል እጥቅም ላይ በዋለበት በማንኛው የብሉይ ኪዳን ክፍል ስታነብ ጥንቃቄ አድርግ፡፡ አዲስ ኪዳን የብሉይ ኪዳን የተስፋ ቃሎች ሁሉ ጥንቅር ነው፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ሁለቱ የእግዚአብሔር መጻሕፍት

ሀ. በአንድ መልኩ የዚህ ልዩ ርዕስ መጠሪያ የሚገልጸው
1. ተፈጥሮ (ማለትም፣ ፍጥረት፣ መዝ. 19፡1-6)
2. ቅዱስ ቃሉ (መዝ. 19፡7-14)

በዚህ ምክንያት ነው እኔ በሳይንስ እና እምነት መካከል በመዳረሻው ላይ ምንም ግጭት አይኖርም ብዬ የማስበው፣ ሁሉም እውነት የእግዚአብሔር እውነት ነው። እባክዎን የእኔን ሐተታ ይመልከቱ፣ ዘፍጥረት 1-11 በነጻ የድረ-ገጽ መስመር www.freebiblecommentary.org

ለ. በመጽሐፍ ቅዱስ የተጠቀሱ ሁለት መጻሕፍት አሉ (ዳን. 7:10፤ ራዕ. 20:12)
1. የሰዎችን ድርጊት ሁሉ የያዘ መጽሐፍ፣ መልካምም ሆነ ክፉ። ይህም የእግዚአብሔርን ማስታወስ የሚያሳይ ዘይቤ ነው፣ አንድ ቀን ሰዎች ሁሉ ለፈጣሪያቸው ምላሽ ይሰጣሉ፣ በሕይወት ስጦታ መጋቢነት በተሰጣቸው።
ሀ. መዝሙር 56:8፤ 139:16

ለ. ኢሳይያስ 65:6
ሐ. ሚልክያስ 3:16
መ. ራዕ. 20:12-13

2. ዝርዝሮች ያሉት መጽሐፍ፣ እምነት/ንስሐ/ታዛዥነት የተሞላ ግንኙነት ከያህዌ/ኢየሱስ ጋር ያላቸው። ይህ የእግዚአብሔር ማስታወስ ዘይቤ ነው፣ የተዋጁትና ሰማያዊ የሆኑት።
ሀ. ዘጸአት 32፡32-33
ለ. መዝሙር 69:28
ሐ. ኢሳይያስ 4:3
መ. ዳንኤል 12:1
ሠ. ፊሊጵስዩስ 4:3
ረ. ዕብራውያን 12:23
ሰ. ራዕይ 3:5፤ 13:8፤ 17:8፤ 20:12,15፤ 21:27
ሸ. ደግሞም 1 ሔኖክ ላይ ተጠቅሷል 47:3፤ 81:1-2፤ 103:2፤ 108:3
እነዚህ መጻሕፍት እግዚአብሔር ለቃሉ ያለውን ታማኝነት ይወክላሉ። የሚያምጹትንና እምቢ የሚሉትን ኃጢአታቸውን ያስብባቸዋል፤ ንስሐ የሚገቡትን፣ የሚያምኑትን፣ የሚታዘዙትን፣ የሚያገለግሉትን፣ እና የሚታገሡትን፣ እሱ ኃጢአታቸውን አያስብም (መዝ. 103:11-13፤ ኢሳ. 1:18፤ 38:17፤ 43:25፤ 44:22፤ ሚኪያስ 7:19)። በርካታ ዋስትናና መተማመን አለ፣ በእግዚአብሔር የማይለወጥ፣ መሐሪ ባሕርይ፣ ተስፋ፣ እና መጋቢነት። እግዚአብሔር የታመነ ነው!

**መዝሙር ፡ 9፡7-10**

**7እግዚአብሔር ግን ለዘላለም ይኖራል፥**
**ዙፋኑንም ለመፍረድ አዘጋጀ።**
**8እርሱም ዓለምን በጽድቅ ይፈርዳታል፥**
**አሕዛብንም በቅንነት ይዳኛቸዋል።**
**9እግዚአብሔርም ለድሆች መጠጊያ ሆናቸው፥**
**እርሱም በመከራቸው ጊዜ ረዳታቸው ነው።**
**10ስምህን የሚያውቁ ሁሉ በአንተ ይታመናሉ፥**
**አቤቱ፥ የሚሹህን አትተዋቸውምና።**

**9፡7-8** አሕዛብ ይመጣሉ ይሄዳሉ፣ ከጻድቁ አምላክ/ፈራጅ ጋር ባላቸው ግንኙነት መሠረት (መዝ. 89፡14)።

## ልዩ ርዕስ፡ ፈራጅ፣ ፍርድ፣ እና ፍትሕ ( ዷፔ –) ኢሳይያስ ላይ

ይህ በሰፋት ጥቅም ላይ የሚውል ቃል ነው (ቢዲቢ 1047) በብኪ። ኒዶቲ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 214፣ የእርሱን ስርጭትና ጠቀሜታውን ያካትታል።

1. ፔንታቲሁች፣ 13%፣ የሰው ፈራጆች
2. የታሪክ መጻሕፍት፣ 34%፣ የሰው መሪዎች
3. የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ፣ 22%፣ መለኮታዊ ድርጊት
4. ነቢያት፣ 31%፣ ባመዛኙ መለኮታዊ ድርጊት

የሚከተለውን ሠንጠረዥ ተመልከት።

| **ያህዌ እንደ ፈራጅ** | **መሢሕ እንደ ፈራጅ** | **የእስራኤል ታሳቢ ፈራጆች** | **የእስራኤል የወቅቱ ፈራጆች** |
|---|---|---|---|
| 2:4 | 9:7 | 1:17,21,23 | 3:2 |
| 3:14 | 11:3,4 | 26:8 | 5:7 |
| 4:4 | 16:5 | 56:1 | 10:2 |
| 5:16 | 32:1 | 58:2,8 | 59:4,9,11,14,15 |
| 28:6,17,26 | 40:14 | | |
| 30:18 | 42:1,3,4 | | |
| 33:5,22 | 51:4,5 | | |
| 61:8 | 53:8 | | |
| 66:16 | | | |

እስራኤል የያህዌን ባሕርይ ለአሕዛብ እንዲያንጸባርቅ ነበር። አልሆነላትም፣ ስለዚህ ያህዌ አንድ "ታሳቢ" እስራኤላዊ አስነሣ፣ የእርሱን አካላዊ መገለጥ በዓለም ለመፈጸም (ማለትም፣ መሢሕ፣ የናዝሬቱ ኢየሱስ፣ ክርስቶስ፣ ኢሳ. 52፡11-53፡12)!

**9:7**
**ኣአመመቅ** **"ይኖራል"**
**አኪጀት** **"ይጸናል"**
**አየተመት፣ አእቅ፣**
**አኢመቅ** **"በዙፋኑ ይቀመጣል"**

*መዝሙር 9:7 ፍጹም ተቃራኒ ነው ለቁ. 5-6።* ዓመጸኞቹ አሕዛብ ጊዜያዊ ናቸው፣ የእስራኤል አምላክ ግን ለዘላለም በዙፋኑ ላይ ሲሆን (ቢ.ዲ.ቢ. 442፣ ኬቢ. 444፣ ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 10:16፤ 29:10)።

*ሁለተኛው ግሥ የቁ. 7፣* "አዘጋጀ" (ቢ.ዲ.ቢ. 465፣ ኬቢ. 464)። የተጠናቀቀ ፖሰል ነው፣ እሱም የእርሱን ዘላለማዊ ዙፋን የሚገልጽ!

**9:8 "እርሱም ዓለምን በጽድቅ ይፈርዳታል፥"** እንደገናም ሥነ-መለኮታዊው ጉዳይ "ዓለም" የሚለው ፍች ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 385)። መዝ. 96:13 እና 98:9 ላይ፣ ይህ ቃል ከ*erets* ጋር ትይዩ ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 75፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር መዝ. 2:2 ላይ)። እሱም የሚያመለክተው በዛን ዘመን "የሚታወቀውን ዓለም ነው። ሆኖም፣ ከአኪ ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ሙሉውን ዓለም ያካትታል (ማለትም፣ ዮሐንስ 3:16)።

**9:9 "መጠጊያ"** ግሡ (ቢ.ዲ.ቢ. 960) ፍችው "ከፍ ማለት" ነው። ስሙ በመደበኛነት ለእግዚአብሔር ከፍታ፣ ብርቱነት፣ እና የደኅንነት መጠጊያ ወይም ምሽግነት ጥቅም ላይ ይውላል (መዝ. 9:9 [ሁለቴ]፤ 18:2፤ 46:7፣11፤ 48:3፤ 59:9፣16፣17፤ 62:2፣6፤ 94:22፤ 144:2)። ይህ የደኅንነት እና የመጠጊያ ፈሊጥ ነው። ለታማኝ ተከታይ (ዝኪ. ቁ. 10) አምላካችን መጠጊያችን ነው፣ ሌላ ምንም የለም!

"በችግር ጊዜ" የሚለውን ሐረግ ተገንዘቡ፣ ቁ. 9ለ ላይ፣ እንደገናም መዝ. 10:1ለ ላይ ይከሰታል። እሱም ብኪ ላይ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው። አንዳንድ ጥርጣሬ አለ፣ "ችግር" ተብሎ ስለተተረጎመው ቃል ፍች (ቢ.ዲ.ቢ. 131)። ኤር. 14:1 እና 17:8 ላይ እሱ የሚለው "ድርቅ" ነው፣ ነገር ግን ያ ፍች እዚህ አይገጥምም። ቃላት በዓረፍተ ነገር ብቻ እንዲሁም ዓረፍተ ነገሮች በጽሑፋዊ ምድቦች ፍች እንዳላቸው አስታውሱ።

**9:10ሀ** ይህ የቅኔ ስንኝ ዋነኛውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነታ ነው የሚገልጸው። የእኔን አስተያየት ከታች አክያለሁ፣ ከኢሳ. 26:3-4። ለዕብራይስጡ ቃል "ማወቅ" ልዩ ርዕስ መዝ. 1:6 ተመልከት።

**ኢሳይያስ 26**
**26:3 "በአንተ ለምትደገፍ ነፍስ ፈጽመህ በሰላም ትጠብቃታለህ"** ኪዳናዊ ገጽታውን ተገንዘብ።

1. የአማኙ ሐሳብ በያህዌ ላይ ዐርፏል (ቢ.ዲ.ቢ. 701፣ ኬቢ. 759፣ ተገብሮ አንቀጽ፣ ግን በአሁን መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ 1 ዜና. 29:18)።
2. ያህዌ እሱን/እሷን ይጠብቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 665 I፣ ኬቢ. 718፣ ያልተጠናቀቀ፣ ኪዳናዊው ግንኙነት ሁለት ተሳታፊዎች አሉት፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት 1:19 ላይ)።
3. "ፍጹም ሰላም" *የሻሎም* ድርብ ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 1022፣ ዝከ ዲኤስኤስ)። ይህ የቃላት ድርቦሽ በዚህ የኢሳይያስ ክፍል ላይ እጅግ የተለመደ ነው።

▣ **"በአንተ ታምኗልና"** "መታመን" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 105፣ ኬቢ. 120፣ ተገብሮ አንቀጽ) ፍችው "በያህዌ መታመን" ነው (ዝኪ. 12:2፤ 26:4፤ 36:15፤ 37:10፤ 50:10)። ቀጣዩ ቁጥር ተመሳሳይ ቃል እንደ ተተኳሪ እንዳለው ተገንዘቡ። ይህ ጠቃሚ የሆነ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ ነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ግላዊ ግንኙነት ስለማስፈለጉ፣ መታዘዝ ብቻ ሳይሆን። ሁለቱም ዋነኞች ናቸው!

**26:4 "ለዘላለም በእግዚአብሔር ታመኑ"** ለግሡ (ቢ.ዲ.ቢ. 105፣ ኬቢ. 120፣ ተተኳሪ)፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት 22:23 ላይ።

በመጀመሪያው መስመር ላይ ቁ. 4 የመለኮቱ ስም ያህዌ ነው፤ ሁለተኛው መስመር ላይ የያህ እና ያህዌ ድብልቅ ነው፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት 1:1 ላይ።

"ዘላለም" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 723 I)፣ በመጀመሪያ የብዙ ቁጥሩ ከዚያም የነጠላ ቁጥሩ (አወቃቀር፣ ዝኪ. 65:18፤ መዝ. 83:18፤ 92:8)። ይህ አወቃቀር፣ ከ"ዘላለም" ጋር (ቢ.ዲ.ቢ. 761)፣ ለያህዌ ጥቅም ላይ የዋለው፣ የሚያመለክተው ከዚህ ሕይወት በኋላ የሚሆነውን ግላዊ ግንኙነት ነው (ዝኪ. ቁ. 14፣19፤ መዝ. 23:6)።

▣ **"የዘላለም ዐለት አለን"** "ዐለት" የሚለው ቃል ዘይቤ ነው፣ ለእግዚአብሔር የማይለወጥ ባሕርይ (መዝ. 18:1፣ 2፤ ኢሳ. 17:10፤ 30:29፤ 44:8)።

**9:10ለ** ለያህዌህ ታማኝነት እንዴት ያለው አስደናቂ ቃል ነው! ይህ የመዝሙር ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (መዝ. 37:28፤ 94:14)። የአማኞች ተስፋ የመሐሪው ፈጣሪ የማይለወጥ ባሕርይ ነው (ሚል. 3:6)።

## ልዩ ርዕስ፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት

1. የሚራራ (ቢ.ዲ.ቢ. 933) – ዘጸ. 34:6፤ ዘዳ. 4:31፤ 2 ዜና. 30:9፤ መዝ. 86:15፤ 103:8፤ 111:4፤ ነህ. 9:17,31፤ ኢዩኤል 2:13፤ ዮና. 4:2

2. ባለ ግርማ (ቢ.ዲ.ቢ. 337) – ዘጸ. 34:6፤ 1 ዜና. 30:9፤ መዝ. 86:15፤ 103:8፤ 111:4፤ ነህ. 9:17,31፤ ኢዩኤል 2:13፤ ዮና. 4:2
3. ለቁጣ የዘገየ (ቢ.ዲ.ቢ. 74 አወቃቀር ቢ.ዲ.ቢ. 60) – ዘጸ. 34:6፤ መዝ. 86:15፤ 103:8፤ ነህ. 9:17፤ ኢዩኤል2:13፤ ዮና. 4:2
4. በፍቅር የተሞላ (ቢ.ዲ.ቢ. 912 I አወቃቀር ቢ.ዲ.ቢ. 338) – ዘጸ. 34:6-7፤ መዝ. 86:15፤ 103:8፤ ነህ. 9:17፤ ኢዩኤል 2:13፤ ዮና. 4:2
5. ታማኝ (ቢ.ዲ.ቢ. 54) – ዘጸ. 4:6፤ መዝ. 86:15
6. በምሕረት የተሞላ (ቢ.ዲ.ቢ. 699)– ነህ. 9:17
7. ያልተዋቸው (ቢ.ዲ.ቢ. 736 I) – ነህ. 9:17,31
8. ለከፋትም የተጸጸተ (ቢ.ዲ.ቢ. 636, ኬቢ. 688, ኒፋል አንቀጽ + ቢ.ዲ.ቢ. 948) – ኢዩኤል 2:13፤ Jon. 4:2
9. ታላቅ አምላክ (ቢ.ዲ.ቢ. 42, 152) – ነህ. 1:5፤ 9:32
10. ታላቅና የሚያስፈራ (ቢ.ዲ.ቢ. 152, 431) – ነህ. 1:5፤ 4:14፤ 9:32
11. ቃል ኪዳኑን የሚጠብቅ (ቢ.ዲ.ቢ. 1036, 136) – ነህ. 1:5፤ 9:32
12. ጽኑ ፍቅር (ቢ.ዲ.ቢ. 338) – ነህ. 1:5፤ 9:32

***መዝሙር ፡ 9፡11-16***

**11በጽዮን ለሚኖር ለእግዚአብሔር ዘምሩ፥**
**በአሕዛብም መካከል አደራረጉን ንገሩ**
**12ደማቸውን የሚመራመር እርሱ አስቦአልና፥**
**የድሆችንም ጩኸት አልረሳምና።**
**13አቤቱ፥ እዘንልኝ፥**
**ጠላቶቼም የሚያመጡብኝን መከራ እይ፥**
**ከሞት ደጆች ከፍ ከፍ የምታደርገኝ**
**14ምስጋናውን ሁሉ እናገር ዘንድ**
**በጽዮን ልጅ በደጆችዋ**
**በማዳንህ ደስ ይለኛል።**
**15አሕዛብ በሠሩት ጒድጓድ ወደቁ፥**
**በዚያችም በሸሸጓት ወጥመድ እግራቸው ተጠመደች።**
**16እግዚአብሔር ፍርድን በማድረግ የታወቀ ነው**
**ኃጢአተኛው በእጆቹ ሥራ ተጠመደ። ሂጋዮን ሴላህ**

**9፡11-12** ያህ ይመሰገናል በፍርዱ ምክንያት (ዝኪ. ቁ. 12፣ 15-16)።

1. ደም ማፍሰስን ይበቀላል
2. የተጨነቀውን ጩኸት አይረሳም

የእርሱ ፍርድ በኃጢአተኛ ክፉ ሐሳብ ላይ ይታያል፣ በእርሱም ራሳቸው የሚጠመዱበት (ዝኪ. ቁ. 15-16)።

**9፡11 "በጽዮን የሚኖር"** ጽዮን የኢየሩሳሌም ተራራ ነው፣ እዚያም የኢያቡሳውያን ምሽግ የነበረበትና በዳዊት የተያዘ። እሱም እዚህ ተራራ ላይ ቤተ-መንግሥቱን ገነባ። ለሙሉ ከተማውም መጠሪያ ሆነ።

ኢየሩሳሌም፣ በተለይም በሞሪያ ተራራ ላይ ያለው መቅደስ፣ ያህዌ "የሚኖርበት" ስፍራ ሆነ፣ በኪሩቤል ክንፎች መካከል፣ ከኪዳን ታቦቱ በላይ። ይህ ስፍራ ዘዳግም ላይ ያለውን ተደጋጋሚ ሐረግ፣ "ያህዌ ስሙ እንዲያደርበት ያዘዘበት ስፍራ" የሚለው ተፈጻሚነት ያገኘበት ነው።

**9፡12**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ደማቸውን የሚጠይቅ"** |
| **አኪጀት፣ አየተመት** | **"ደማቸውን የሚበቀል"** |
| **አኢመቅ፣ የተእመቅ** | **"የደማቸው ተበቃይ"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ደም ማፍሰስን የሚመራመር"** |

ይህ ሐረግ ከዘፍ. 9፡5-6 ጋር ይያያዛል። ሕይወት ከእግዚአብሔር የሆነ ስጦታ ነው። ማንም ያንን ስጦታ የሚወስድ በእግዚአብሔር ፊት ምላሽ መስጠት ይኖርበታል፣ እናም በገዛ ሕይወቱ/ሕይወቷ ይከፍላል (ዘዳ. 32፡43)።

ኋላ ላይ ይህ በዕብራውያን አስተሳሰብ “ደም ተበቃይ” ወደሚል እየጎለበተ መጣ (ማለትም፣ ኢያ. 20፡3፣5፣9)።

▣ **“አስቦአልና... አልረሳምና”** “ማሰብ” ከ “መርሳት” (አሉታዊ) ጋር እንዴት ትይዩ እንደሆነ ተገንዘቡ። እርሱ ሕዝቡን አይረሳም!

**9፡13-14** ከፉው የመዝሙረኛውን ነፍስ ይሻል (ማለትም፣ ንጉሥ) ያህዌ ግን አዳነው። አሁን ያህዌን ሊያመሰግን ይሻል፣ በማደሪያው ድንኳን/በመቅደሱ (“በጽዮን የሚኖረው” ቁ. 11)።

1. “እኔም እናገራለሁ” — ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765፣ ተጓዳኝ
2. “እኔም እደሰታለሁ” — ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189፣ ተጓዳኝ

**9፡13 “የሞት ደጆች”** ሲኦል (ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 6፡5 ላይ) የተገለጸውም እንደ

1. እንደ ተከፈተ መቃብር/ጉድጓድ (ዘጸ. 15፡12፤ ዘኍ. 16፡22፤ 26፡11፤ መዝ. 124፡3፤ ምሳ. 1፡12)
2. ሥጋ በል አውሬ ኢሳ. 5፡14፤ ዕን. 2፡5)
3. ደጅ ያላት ከተማ (ኢዮብ 38፡17፤ መዝ. 107፡18፤ ኢሳ. 38፡10፤ ማቴ. 16፡18) ወይም
4. ደጅ ያለው ወኅኒ (ራዕ. 1፡8፤ 9፡1፤ 20፡1)

**9፡14 “በጽዮን ልጅ በደጆችዋ”** ግልጽ የሆነ ተቃርኖ አለ፣ “በሞት ደጆች” ቁ. 13ሐ እና የኢየሩሳሌም/መቅደስ ቁ. 14ሐ መካከል። በመጀመሪያው መታሰቢያ የለም፣ ነገር ግን በሁለተኛው ምስጋና እና መታሰቢያ አለ፣ ለያህዌ።

**9፡15-16** የስድስቱን የተጠናቀቁ ጊዜያት ድርደራ ተገንዘብ። የጠላት ሠራዊት በያህዌ መሸነፍ (ማለትም፣ ቅዱስ ጦርነት፣ ምናባዊ ድል) አትኩሮት ነው።

**9፡15** የመዝሙረኛው ጠላቶች ሕዝቦች መሆናቸውን ተገንዘብ (ዝከ. ቁ. 17) ግለሰቦች ሳይሆኑ። ስለዚህ፣ ይህ ንጉሥ መሆን አለበት፣ ስለዚህ ልማዳዊው መግቢያ ትክክል ሊሆን ይችላል።

**9፡16** በብኪ የእግዚአብሔር ባሕርይ የሚገለጠው በጊዜ ውስጥ ነው፣ በድርጊቶቹ።

1. ጸጋ፣ ምሕረት፣ እና ፍቅር ለኪዳኑ ሕዝቦች
2. ፍርድ እና ቁጣ በጠላቶቹ ላይ

የከፉው ሐሳብ (ዕቅድ) መገልበጡን ተገንዘብ። በሌሎች ላይ ያሰቡት በራሳቸው ላይ ሆነ። ፍርድ በእግዚአብሔር የፍጥረት ሥርዓት ላይ ተገንብቷል።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት፣** | |
| **አየተመት፣ ጀፒኤስአኤ** | **“ተጠመደ”** |
| **አእቅ፣ የተእመቅ** | **“ተጠመደ”** |
| **አኢመቅ** | **“በወጥመድ”** |
| **LXX** | **“ወጥመድ”** |

ኤምቲ “ተመታ” የሚል አለው ከቢዲቢ 669፣ ኬቢ 723፣ የድርጊት አንቀጽ (በብኪ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው)። ሁሉም የእንግሊዝኛ ትርጉሞች እሱን የሚመለከቱት እንደ ኒፋል የተጠናቀቀ ነው፣ የቢዲቢ 430፣ ኬቢ 432፣ “መጠመድ” ወይም “ማጥመጃ።” የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 171) ለኤምቲ ደረጃ “ሐ” ይሰጠዋል (ምክንያታዊ ጥርጣሬ)።

▣ **“ሂጋዮን”** ቢዲቢ (212፤ የመዝሙር መግቢያ VII ማስታወሻ ተመልከት) ይህንን የሚገልጸውም እንደ

1. የሚያስተጋባ ዜማ (መዝ. 92፡3)
2. ምልጃ፣ ጸጥታ (መዝ. 19፡14)

እሱም ሰቆ. 3፡62 ላይ እንደ “የለሆሳስ ንግግር” በሚል ተተርጉሟል (ኬቢ 238)።

▣ **“ሴላህ”** መዝሙር 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

***መዝሙር ፡ 9፡17-20***

**17ኃጢአተኞች ወደ ሲኦል ይመለሳሉ፥**
**እግዚአብሔርን የሚረሱ አሕዛብም ሁሉ።**
**18ድሀ ለዘላለም አይረሳምና፥**
**የችግረኞችም ተስፋቸው ለዘላለም አይጠፋም።**
**19አቤቱ፥ ተነሥ ሰውም አይበርታ፥**
**አሕዛብም በፊትህ ይፈረድባቸው።**

[20]**አቤቱ፥ ፍርሃትን በላያቸው ጫንባቸው**
**አሕዛብ ሰዎች እንደ ሆኑ ይወቁ።** **ሴላህ**

**9፡17-18** *ኃጢአተኛ በሞኝነት እንደሚያደርግ (ማለትም፣ ወደ ሲኦል መመለስ)፣ (ችግረኛ (ቢዲቢ 2) እና መከራ ተቀባይ (ቢዲቢ 776፣ "ደሀ") በያህዌ ይታገዛሉ።*

**9፡17 "እግዚአብሔርን የሚረሱ አሕዛብ ሁሉ"** አብዛኞቹ የእስራኤል ጠላቶች የአካባቢው አሕዛብ ነበሩ፣ ስለ ያህዌ በመጠኑ የሚያውቁ። "መርሳት" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 1013) የሚያመለክተውም ከእውነት ዞር እንዳሉ ነው፣ በአንድምታውም፣ ሐሰተኛ ጣዖቶችን እንዳመለኩ።

**9፡19-20** እነዚህ የመጨረሻ ሁለቱ ስንኞች፣ ያህዌ እንዲያደርግ ተለጣጣቂ ቃላትን ይዘዋል።

1. *ተነሥ* – ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ ተተኳሪ (በተቃራኒውም ለመዝ. 9፡4ለ፣7፣ እዚያም በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው፣ ለመለኮታዊው ተዋጊ ድርጊት ጥሪ ማድረግ)
2. ሰውም አይበርታ – ቢዲቢ 738፣ ኬቢ 808፣ ያልተጠናቀቀ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. አሕዛብም በፊትህ ይፈረድባቸው – ቢዲቢ 1047፣ ኬቢ 1622፣ ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
4. ፍርሃትን በላያቸው ጫንባቸው – ቢዲቢ 1011፣ ኬቢ 1483፣ ያልተጠናቀቀ
5. አሕዛብ ሰዎች እንደሆኑ ይወቁ – ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ ያልተጠናቀቀ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ (መዝ. 62፡9፤ 90፡5-6፤ 103፡14፤ ኢሳ. 40፡7-8)

**9፡20 "ሴላህ"** *መዝሙር 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።*

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወስን አይደለም።

1. ቁጥር 3 የፍርድ-ቤት ትዕይንት ለምን ሆነ?
2. "አሕዛብ" እና "ክፉ" ቁጥር 5 ላይ እንዴት ይዛመዳሉ?
3. ቁጥር 13 እና 14 ላይ ያሉትን የተለያዩ "ደጆች"ን ግለጽ።
4. ሲኦልና ጥልቁ እንዴት ይዛመዳሉ?

# መዝሙር 10
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጸሎት ለክፉዎች መወገድ | የእምነት መዝሙር አምላክ በክፉው ላይ ባገኘው ድል | ከግል ጠላቶች ስለመታደግ ጸሎት (መዝሙር 9-10፣ ሰቆቃ) መስቀልያ | ስለ ፍትሕ ጸሎት | አምላክ ክፉዎችን ይመታል ትሑታንን ይታደጋል መዝ.9-10 የቀጠለ መስቀልያ |
| የኤምቲ መግቢያ የለውም | | | | |
| | 10:1-2 | 10:1-2 | 10:1-2 | |
| 10:1-2 | | | | 10:1-2 (ላሜድ) |
| | 10:3-4 | 10:3-4 | 10:3-4 | |
| 10:3-4 | | | | 10:3 (ሜም) |
| | | | | 10:4 (ነን) |
| | 10:5-7 | 10:5-6 | 10:5-7 | |
| 10:5-11 | | | | 10:5 |
| | | | | 10:6ሀ፣ለ |
| | | | | 10:6ሐ-7ሀ |
| | | 10:7-8ሀ | | |
| | | | | 10:7ለ-8ለ (ፒ) |
| | 10:8-11 | 10:8ለ-9 | 10:8-9 | |
| | | | | 10:8ሐ-9 (ኤይን) |
| | | 10:10-11 | 10:10-11 | |
| | | | | 10:10-11 |
| | 10:12-13 | 10:12-13 | 10:12-13 | |
| 10:12-15 | | | | 10:12-13 (ቆፍ) |
| | 10:14-15 | 10:14 | 10:14 | |
| | | | | 10:14 (ረሽ) |
| | | 10:15-16 | 10:15 | |
| | | | | 10:15-16 (ሽም) |
| | 10:16-18 | | 10:16 | |
| 10:16-18 | | | | |
| | | 10:17-18 | 10:17-18 | |
| | | | | 10:17-18 (ታው) |

## የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

# የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 10:1-2**

**1 አቤቱ፥ ለምን ርቀህ ቆምህ?**
**በመከራም ጊዜ ለምን ትሰወራለህ?**
**2 በኃጢአተኛ ትዕቢት ድሀ ይናደዳል**
**ባሰቡት ተንኰላቸው ተጠመዱ።**

**10፡1** ይህ የተለመደ ጥያቄ ነው፣ ለታማኝ አማኞች በወደቀው ዓለም። ክፉና መከራ ዘወትር ያስገርማሉ፣ እንዲሁም ያልተጠበቁ ሁነቶች። የሚወደን መሐሪ አምላክ ይህ እንዲሆን ለምን ይፈቅዳል?

ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምላሽ አይኖርም፣ በወደቀው ዓለም ውስጥ ከመኖራችን በቀር። ይህ፣ እግዚአብሔር እንዲሆን የፈለገው ዓለም አይደለም፣ አልያም ወደፊት የሚመጣውም ዓለም አይደለም። እንደ ሥነ-መለኮታዊነቴ ማስረገጥ የሚኖርብኝ፣ እግዚአብሔር የሁለቱንም አዳምና/ሔዋን ኃጢአት መዘዝ እንድናጭድ ይፈቅዳል፣ እንዲሁም የራሳችንን የግል ምርጫዎች። እሱም በእኛ በኩል ለመዋጀታችን ጠንክሮ ይሠራል! በዚህ ሕይወት/ዓለም ላይ በክፉውና በመከራ ርዕሰ-ጉዳይ ላይ የተሻለው መጽሐፍ፣ እሱም በርግጥ በምር የወሰደው፣ የጆን ደብልዩ. ዌንሀም፣ *የእግዚአብሔር መልካምነት* ነው።

▣ ዘማሪው ሁለት የተለዩ ጥያቄዎችን ይወስዳል ("ለምን") ስለ እግዚአብሔር አጠቃላይ መቅረት።

1. ርቆ መቆም – ቢ.ዲ.ቢ. 763፣ ኬቢ. 840፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
2. ራስን መደበቅ – ቢ.ዲ.ቢ. 761፣ ኬቢ. 834፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 27:9፤ 55:1፤ 69:17

ያህዌ ተስፋ ሰጥቷል፣ ከኪዳኑ ሕዝብ ጋር ለመገኘት እና ለመሳተፍ፣ ነገር ግን የቀረና ሆን ብሎ ዝም ያለ ይመስላል (መዝ. 10፡5ሀ፣11)!

የድምጹን ለዛና ትይዩአዊነት የANE ቅኔ ባሕርይ እንደሆነ ተገንዘብ (ዕዝል ተመልከት፡ የዕብራይስጥ ቅኔ)።

እነዚህ ቃላት ከእውነታው አይደሉም፣ ነገር ግን የተደነጋገሩና የተጎዱ አማኞች ስሜቶች እንጂ።

**10፡2** የክፉዎችን ባሕርይ ተገንዘብ።

1. ኩራት/ትዕቢት – ቢ.ዲ.ቢ. 144፣ መዝ. 31:18፣23፤ 36:11፤ 73:6
2. ጥላቻን መከተል – ቢ.ዲ.ቢ. 196፣ ኬቢ. 223፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ ዘፍ. 31:36፤ 1 ሳሙ. 17:53፤ ሰቆ. 4:19
3. ተንኮለኝነት – ቢ.ዲ.ቢ. 362፣ ኬቢ. 359፣ *ቃል* የተጠናቀቀ

ይህ በቀጣዮቹ አንጓዎች እየዳበረ ይሄዳል (ቁ. 3-4 እና 5-11)።

▣ **"ባሰቡት ተንኰላቸው ተጠመዱ።"** ይህ በአአመመቅ የተተረጎመው እንደ ተጽዕኗዊ ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 1074፣ ኬቢ. 1779፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ)፣ እንደ መዝ. 10:15ለ እንዲሆን።

ይህ የሚገልጸው ሁነኛውን የብኪ ሐሳብ ነው፣ "ማሳያ የተገላቢጦሽ።" የተጠበቀው ነገር አይከሰትም፣ ከእግዚአብሔር መገኘት የተነሣ።

---

***መዝሙር ፡ 10፡3-4***

**[3]ኃጢአተኛ በነፍሱ ፈቃድ ይወደሳልና፥**
**ዓመፀኛም ይባርካል።**
**[4]ኃጢአተኛ እግዚአብሔርን አበሳጨው፥**
**እንደ ቍጣውም ብዛት አይመራመረውም**
**በእርሱ ፊት እግዚአብሔር የለም።**

---

**10፡3-4** ይህ አንጓ በተጨማሪ የሚገልጸው (1) ጣዖት አምላኪዎችን፣ (2) አምላክ-የለሾችን፣ ወይም ቢያንስ (3) "በተግባራቸው አምላክ-የለሽ" የሆኑትን የመዝሙረኛውን ጠላቶች ነው (ማለትም፣ ሌሎች እስራኤላውያንን)።

1. የጌታ ርግማን — ነገር ግን ለጥቂት ጊዜ "ርግማን" በሚል መልኩ፣ (ጽሑፍ "ባርኮት፣" ቢ.ዲ.ቢ. 138፣ ኬቢ. 159፣ *ፒዬል* የተጠናቀቀ፣ ዝከ. 1 ነገ. 21:10፣13፤ ኢዮብ 1:5፤ 2:9)
2. እግዚአብሔርን መናቅ – ቢ.ዲ.ቢ. 610፣ ኬቢ. 658፣ *ፒዬል* የተጠናቀቀ
3. ጌታን አለመፈለግ – ቢ.ዲ.ቢ. 205፣ ኬቢ. 233፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
1. እግዚአብሔር እንደሌለ ማሰብ – "የለም፤" ቢ.ዲ.ቢ. 34 ll፣ "እግዚአብሔር፣" ቢ.ዲ.ቢ. 43 (ሐረጉ ግስ የለውም)፣ ዝከ. መዝ. 10:5ሀ፣11፤ 14:1፤ 53:1፤ ይህ ፍልስፍናዊ ጉዳይ አይደለም፣ ነገር ግን ተግባራዊ ጉዳይ ነው። በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ (ጥቅም) የነበረ ሁሉ በመንፈሳዊ ግዛት ያምናል። ጀፒኤስኦኤ ሐረጉን የሚተረጉመው "እግዚአብሔር እንደማይገደው" ነው።

**10፡3ሀ** የዘፍጥረት 3 ውድቀት የፍጥረትን ልብ ከፈጣሪ አራቀው፣ ብሎም ወደ ገዛ ራሱ/ገዛ ራሷ አደረጋቸው። ሕይወታችን የሚባክነው ግላዊ የሆኑ ነገሮችን፣ ሥልጣንን፣ እና ኃይልን በመፈለግ ነው። አውግስጢኖስ ደኅና አድርጎ አስቀምጦታል፣ እያንዳንዱ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ቅርጽ አምሳል (ሞልድ) ነው የተፈጠረው ሲል። እግዚአብሔር ብቻ ነው ያንን መሻት ሊሞላ የሚችለው፣ ነገር ግን የወደቀው ሰው ሊሞላው ይሞክራል፣ በጊዜያዊ/ምድራዊ ነገሮች።

---

***መዝሙር ፡ 10፡5-11***

**[5]*መንገዱ ሁሉ የረከሰ ነው፥***
**ፍርድህም በፊቱ የፈረሰ ነው፥**
**ጠላቶችንም ሁሉ ይገዛቸዋል።**
**[6]በልቡ ይላል። ለልጅ ልጅ አልታወክም**

---

ከፉም አያገኘኝም።
7አፉ መርገምንና ሽንገላን ተንኰልን የተመላ ነው
ከምላሱ በታች ጒዳትና መከራ ነው።
8በመንደሮች መሸመቅያ ይቀመጣል
ንጹሓንን በስውር ይገድል ዘንድ
ዓይኖቹም ወደ ድኃ ይመለከታሉ።
9እንደ አንበሳ በችፍግ ዱር በስውር ይሸምቃል
ድሀውን ለመንጠቅ ያደባል ድሀውን ይነጥቀዋል
በአሽክላውም ይስበዋል።
10ድሀ ይዋረዳል፥ ይጐብጣል
በኃያላኑም እጅግ ይወድቃል።
11በልቡም ይላል። እግዚአብሔር ረስቶኛል
ፈጽሞም እንዳያይ ፊቱን ሰወረ።

**10፡5-11** ይህ አንጓ የሚገልጸው የሕይወትን ፍትሐዊ አለመምሰል ነው። ኃጢአተኞች ይሳካላቸዋል፣ ጻድቃን ደግሞ መከራ ይቀበላሉ! ተመሳሳይ ጉዳይ በመጽሐፈ ኢዮብ፣ መዝሙር 73፣ እና ዕንባቆም ላይ ተመልክቷል። የኃጢአተኞች ባሕርይ የተገለጸው እንደ፡

1. ሁል ጊዜ ይሳካላቸዋል — ግሥ (ቢዲቢ 298 II፣ ኬቢ 311፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) ጽሑፉ "ጽና፣" ነው፣ ነገር ግን ጥቅም ላይ የዋለው ለብልጽግና በሚል ነው፣ ዘፍ. 34:29፤ ዘኍ. 31:9፤ ዘዳ. 8:17፣18፤ ኢዮብ 5:5፤ 15:29፤ 20:15፣18፤ 31:25፤ መዝ. 49:6፣10፤ 62:10፤ 73:12፤ ኢሳ. 8:4፤ 10:14፤ 30:6፤ 60:5፤ 61:6፤ ሚኪያስ 4:13
2. በባላንጣው ላይ እያፌዘ ይስቃል – ቢዲቢ 806፣ ኬቢ 916፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*፣ ይህን መሰል መልኩ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው ነገር ግን ቃሉ ለሐሰተኞች ዘወትር ምሳሌ ላይ ጥቅም ላይ ይውላል (ምሳ. 6:19፤ 14:5፣25፤ 19:5፣9)
3. አልናወጥም – ቢዲቢ 556፣ ኬቢ 555፣ *ኒፉል ያልተጠናቀቀ*፣ ፍችውም የብልጽግና ሁኔታዬ እና ደኅንነቴ ፈጽሞ አይለወጥም
4. አፉም የተሞላ ነው (ማለትም፣ አፍ ልቡናን ይገልጻል፤ ጳውሎስ ይሄንን ቁጥር ይጠቅሳል፣ በብኪ ጽሑፎች ገለጻው ላይ፣ እነርሱም የሰውን ኃጢአት ሁለንተናዊነት የሚገልጡ፣ ሮሜ 3፡14)
   ሀ. ርግማን
   ለ. ማሳት
   ሐ. መጨቆን
   መ. ማታለል
   ሠ. ኃጢአተኝነት
5. እሱም በንጹሐን ላይ እንደ ዱር አውሬ ያሸምቃል (መዝ. 10:8-10፤ ሰቆ. 3:10-11)
6. እሱም የመዝሙረኛውን ሁነኛ ቃላት ያምናል ያስረግጣልም፣ ከቁ. 1። አምላክ ቀርቷል፣ አልረዳንምም! የመዝሙረኛው ቃላት የእምነት ጩኸት ነው፣ ነገር ግን የማያምኑትም ማስረገጫዎች አሉ (መዝ. 39፡1-2)።

**10፡5ለ** ይህ የቅኔ ሐረግ እግዚአብሔር እንደራቀና እንደማይረዳ አድርጎ ነው የሚጠቅሰው (ዝከ. ቁ. 4ለ፣11)።

**10፡8 "መንደሮች"** ይህ ከዐውደ-ጽሑፉ ጋር የሚገጥም አይመስልም፣ አኢመቅ አናባቢዎቹን ይቀይራቸዋል፣ ወደ "ደንገላማ" (UBS ጽሑፍ ፕሮጀክት፣ ገጽ 174 ለ"መንደር" "ለ" ደረጃ ይሰጣል፣ ፍችውም "መጠነኛ ጥርጣሬ")። አእት መጽሐፍ ቅዱስ የሚተረጉመው "ከመንደሮች አቅራቢያ" ነው (ኤምቲ. "በመንደሮች")።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ የተእመቅ** | **"ያልታደለ"** |
| **አአመመቅ የግርጌ** | **"ምስኪን"** |
| **አኪጀት፣ አየተመት** | **"ረዳት አልባ"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ረዳት አልባ"** |
| **LXX** | **"ችግረኛ"** |

ይህ ቅጽል (ቢዲቢ 319፣ ኬቢ 319) የሚከሰተው በመዝሙር ላይ እዚህ ምዕራፍ ላይ ብቻ ነው፣ እንዲሁም በአኪ ሦስት ጊዜ ብቻ። እንደሚመስለኝ ሦስቱም የሚጠቅሱት ስለ ተጠቃ ሰው ነው።

**መዝሙር ፡ 10፡12-15**
12አቤቱ አምላክ ሆይ፥ ተነሥ
እጅህም ከፍ ከፍ ትበል
ድሆችን አትርሳ።

**[13]ኃጢአተኛ ስለ ምን እግዚአብሔርን አስቈጣው?**
**በልቡ። አይመራመረኝም ይላልና።**
**[14]አየኸው፥ አንተ ክፋትንና ቍጣን ትመለከታለህና**
**በእጅህ ፍዳውን ለመስጠት ድሀ ራሱን ለአንተ ይተዋል፥**
**ለድሀ አደግም ረዳቱ አንተ ነህ።**
**[15]የኃጢአተኛንና የክፉን ክንድ ስበር፥**
**የኃጢአቱንም ብድራት ክፈል**
**ሌላ እስከማይገኝ ድረስ።**

**10፡12** ይህ ቁጥር የሚገልጸው ማድባትን ነው (*ቆሪ*) ለዱር አውሬ፣ ሰለባ (ታዳኝ) ለመፈለግ።

**10፡12-15** ይህ ለእግዚአበሔር ጸሎት ነው፣ እንዲያደርግ።
1. ተነሥ — (ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ *ቃል ተተኳሪ*) ከዙፋንህ ላይ ወይም እንደ መለኮታዊ ተዋጊ
2. እጅህን ዘርጋ – ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. ምስኪኑን አትርሳ – ቢዲቢ 1013፣ ኬቢ 1489፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 9:12 እና 19 ይቃረናል መዝ. 10:11!
4. የኃጢአተኛውን ክንድ ስበር – ቢዲቢ 990፣ ኬቢ 1402፣ *ቃል ተተኳሪ* (ማለትም፣ ኃይሉን ስበር የዚህን/የእነዚህን ክፉ ሰው/ሰዎች)
5. ፈልግ – ቢዲቢ 205፣ ኬቢ 233፣ *ቃል ተተኳሪ* በተተኳሪ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

መዝሙረኛው፣ እግዚአብሔር በታመነ አማኝ አኳያ እንዲሠራ ይፈልጋል፣ ለኃጢአተኛው ሞኝነቱን ለማሳየት!

***መዝሙር* ፡ 10፡16-18**
**[16]እግዚአብሔር ለዘላለም ይነግሣል**
**አሕዛብ ከምድሩ ይጠፋሉ።**
**[17]እግዚአብሔር የድሆችን ምኞት ሰማ፥**
**ጆሮውም የልባቸውን አሳብ አደመጠች፥**
**[18]ፍርዱ ለድሀ አደግና ለችግረኛ ይደረግ ዘንድ፥**
**ሰዎች በምድር ላይ አፋቸውን ከፍ ከፍ ማድረግ እንዳይደግሙ።**

**10፡16-18** ይህ አንጓ የሚያስረግጠው የእስራኤልን አምላክ ባሕርይ ነው፣ ፈጣሪው፣ የሚቤዠው አምላክ።
1. ያህዌ ለዘላለም ይነግሣል (ዘጸ. 15:18፤ መዝ. 9:7፤ 29:10፤ 146:10፤ ኤር. 10:10፤ ሰቆ. 5:19)። ለ “ዘላለም” መዝ. 9፡5 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።
2. ያህዌ ለእስራኤላውያን የከነአንን ምድር ሰጣቸው (ዘፍ. 15፡12-21)። “በአሕዛብ” ላይ ማተኮሩ መዝ. 9፡17-20 ያለውን ሐሳብ ለማጠቃለል ይመስላል።
3. ያህዌ ትሑት/የተቸገረ አማኝን ይሰማል፣ ለእርሱ ብሎም ይተገብራል (የተጠናቀቀውን ተገንዘብ፣ ያህዌ ይሰማል ሰምቷልም)።
4. ያህዌ በማኅበራዊ ደካማ በሆኑትና ለተጋለጡት ጎን ይተገብራል (ማለትም፣ ዘዳግምን የሚያንጸባርቅ)።
5. ያህዌ የማያምነውን ትዕቢተኛ እና የእርሱን/እሷን ሥራ ከምድር ያስወግዳል።

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት፣ መዝ. 9፡10ለ ላይ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።
1. ቁጥር 4 የሚገልጸው አምላክ-የለሽን ነው?
2. ቁጥር 6 ላይ ያለው ግለሰብ የሚያስረግጠው ምንድነው?
3. ቁጥር 11 እና 13ለ ላይ ያለው ግለሰብ የሚያስረግጠው ምንድነው?
4. ቁጥር 18 ከዘዳግም ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?

## መዝሙር 11
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ መጠጊያና መከለያ | በእግዚአብሔር ጽድቅ መታመን | አምላክ ለፍትሕ እንደሚገደው መታመን | በእግዚአብሔር መታመን | የጻድቅ መተማመኛ |
| ኤምቲ መግቢያ<br>"ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር" | | | | |
| | 11:1-3 | | | |
| 11:1-3 | | 11:1-3 | 11:1-3 | 11:1 |
| | | | | 11:2-3 |
| | 11:4-6 | | | |
| 11:4-7 | | 11:4-7 | 11:4-5 | 11:4 |
| | | | | 11:5-6 |
| | | | 11:6-7 | |
| | 11:7 | | | |
| | | | | 11:7 |

### **የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

# የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 11፡1-3**
**[1]በእግዚአብሔር ታመንሁ ነፍሴን።**
**እንደ ወፍ ወደ ተራሮች ተቅበዝበዝ እንዴት ትሉአታላችሁ?**
**[2]ኃጢአተኞች እነሆ ቀስታቸውን ገትረዋልና፥**
**ፍላጻቸውንም በአውታር አዘጋጅተዋልና፥**
**ልበ ቅኖችን በስውር ይነድፉ ዘንድ።**
**[3]አንተ የሠራኸውን እነሆ እነርሱ አፍርሰዋልና**
**ጻድቅ ግን ምን አደረገ?**

**11፡1 "መጠጊያ"** መዝ. 2:12፤ 5:11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት። ይህ (ቢዲቢ 340፣ ኬቢ 337፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) አስደናቂ ተደጋጋሚ ዘይቤ ነው፣ ለመጠበቂያና ለደኅንነት (ዝኪ. 34:22፤ 37:40፤ ሕዝ. 7:15-16)።

የዳዊት ባላንጣዎች (ወይም ጠላቶች) "ሽሽ" ብለዋል (ቁ. 1ለ)፣ ዳዊት ግን፣ "ለምን እሸሻለሁ?" ብሏል (ቁ. 1ሀ፣ 2-3)። እግዚአብሔር በጠጊያችን ነው፣ በምን ውስጥ እንደምናልፍም ያውቃል። እሱ ከእኛ ጋር እና ለእኛ ነው። እሱን ተመልከቱ፣ ሁኔታዎችን ሳይሆን!

▣ **"እንደ ወፍ ወደ ተራሮች ተቅበዝበዢ"** ኤምቲ (ማሶረቲክ ጽሑፍ) የብዙ ቁጥር አለው (ቢዲቢ 626፣ ኬቢ 678፣ *ቃል ተተኳሪ*)። ነገር ግን የ*ቁሪ ንባብ* ነጠላ ቁጥር ነው።

ሊሆን የሚችለውም፣ ክፉ (ማለትም፣ የብዙ ግሥ) ታማኙን ወደ ያህዌ መጠጊያ እንዲሸሽ ይነግረዋል (ማለትም፣ "መጠጊያ" እና "ተራራ" ትይዩ ናቸው፣ መዝ. 121፡1)። ስለዚህ ሐረጉ ማስፈራሪያ ነው።

የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ የሚለው ቁጥር 1 እና 4 የሚከሰተው መቅደስ ላይ ነው፣ እና ስለዚህ፣ የዘማሪው ባልንጀሮች/የአምልኮ ባልደረቦች ናቸው፣ ጸጥ ብሎ ወደ ምድረ-በዳ ምሽግ እንዲሸሽ የሚነግሩት።

እንደሚመስለኝ፣ "መሠረቶች" መዝ. 11፡3 ላይ ያለው ደግሞ "ከመጠጊያ" እና "ተራሮች" ጋር ትይዩ ነው። እነርሱ የሚያመለክቱት የያህዌን መገኘትና እውነት ነው (ዝከ. 87፡1፤ 119፡152) ከሕዝቡ ጋር፣ ይኸውም ከፉዎች የካዱትን።

**11፡2-3** እነዚህን ቁጥሮች በሁለት መንገዶች መመልከት ይቻላል።

1. (ሀ) የክፉዎች ምክር ወይም (ለ) የአምልኮ ባልንጀሮች፣ እስከ ቁ. 3 የሚቀጥል
2. መዝሙረኛው እንዲሸሽ ለሚነግሩት ይመልስላቸዋል፣ ቁ. 1ለ

**11፡2** ይህ የሚገልጸው የክፉዎችን ጎጂ ድርጊትና ዕቅድ ነው።

1. ቀስታቸውን ገተሩ – ቢዲቢ 201፣ ኬቢ 131፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 7፡12፤ 37፤14
2. ፍላጻዎቻቸውን በአውታር አዘጋጅተዋል – ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 464፣ *ፖለል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 64፡3
3. መንደፍ – ቢዲቢ 434፣ ኬቢ 436፣ *ቃል* ያልተወሰነ ግንባታ፣ መዝ. 64፡6

▣ **"ልበ-ቅን"** ኃጢአት-የለሽ ሰው የለም። ሆኖም፣ በግልጽ ሁለት ዓይነቶች አሉ።

1. ያህዌን የሚፈልጉና እሱን ለማስደሰት የሚኖሩ
2. ለራሳቸው የሚኖሩ፣ ምንም ዓይነት ኪዳን ወይም የኪዳን አምላክ እንደሌለ አድርገው

**11፡3** የጻድቅ ሰው ብቸኛ ተስፋ የያህዌ እውነትና መገኘት ነው። እሱ ብቻውን የረድኤት ምንጭ ነው! አምላክ ከሌለ (መዝ. 10፡4፤ 14፡1፤ 36፡1) እንግዲያውስ ታማኝ ተከታይ ሞኝ ነው፣ ነገር ግን ሥነ-ምግባራዊ ፈጣሪ ካለ፣ በእርሱም ፊት ሁሉም ባለ ንቁ ሕሊና የሚቆምና መልስ የሚሰጥ (ዝከ. ቁ. 4ለ-ረ) እንግዲያውስ የማይታዘዝ፣ ክፉ፣ ራስ-ወዳድ ሰው (ጣዖት አምላኪ ወይም እስራኤላዊ) ሞኝ ነው!

የቁ. 3 ሁለተኛው መስመር እግዚአብሔርን የሚያመለክትበት አጋጣሚ አለ (ማለትም፣ "ጻድቁ፣" ዝከ. AB፣ ገጽ 69፣ እና በአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ የግርጌ ማስታወሻ፣ ገጽ 1294)። መዝ. 11፡5 ተመልከት፣ እዚያም ያህዌ እና ጻድቅ (ቢዲቢ 843) በተቃውሞ የሚሆኑበት፤ ሁለቱም ለእስራኤል አምላክ መጠሪያዎች ናቸው።

▣ ***"መሠረቶች"*** የዚህ *ቃል/ሥር*፣ *ሥርወ-ቃል*፣ שׁת (ቢዲቢ 1011፣ ኬቢ 1666-1667)። እሱ የአልፎ አልፎ ቃል ሲሆን፣ የጋራ መግባባት ያለው የኪዳን ሕግጋትን እንደሚጠቅስ ነው። ኬቢ የቅርብ ምሑራዊ ግምቶች አለው።

***መዝሙር ፡ 11፡4-7***

**4 እግዚአብሔር በተቀደሰው መቅደሱ ነው**
**እግዚአብሔር፥ ዙፋኑ በሰማይ ነው**
**ዓይኖቹ ወደ ድሃ ይመለከታሉ፥**
**ቅንድቦቹም የሰው ልጆችን ይመረምራሉ።**
**5 እግዚአብሔር ጻድቅንና ኀጥእን ይመረምራል**
**ዓመፃን የወደዳት ግን ነፍሱን ጠልቶአል።**
**6 ወጥመድ በኀጥኣን ላይ ያዘንባል**
**እሳትና ዲን ዐውሎ ነፋስም የጽዋቸው እድል ፈንታ ነው።**
**7 እግዚአብሔር ጻድቅ ነውና፥**
**ጽድቅንም ይወድዳል**
**ቅንነት ግን ፊቱን ታየዋለች።**

**11፡4-7** ይህ አንጓ በክፉው ለተሰነዘረው ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል፣ መዝ. 11፡1ለ ላይ። እንደሚሆነው፣ "መሠረቶች" የቁ. 3ለ አልተደመሰሱም!

**11፡4** ያህዌ በሰማይ ይኖራል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 8፡1 ላይ)፣ ነገር ግን እሱ ራሱን ይገልጣል (ማለትም፣ ራሱን እንዲገኝ ያደርጋል) በኪሩቤል ክንፎች መካከል፣ ከኪዳኑ ታቦት በላይ (ኢሳ. 66፡1)። ሰማይና ምድር በቅድስተ ቅዱሳን በኢየሩሳሌም መቅደስ ይገናኛሉ።

**11፡4ለ-5ሀ** ያህዌ ያውቃል (ያልተጠናቀቀ፣ ባሕርያዊ ድርጊትን የሚገልጽ)

1. በምድር ላይ ምን እንደሚሆን
2. የሰው ልብ ሐሳብ

እሱ ይፈትናል (ቢ.ዲ.ቢ. 103፣ ኬቢ. 119፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*፣ ኢዮብ 7:18፤ መዝ. 7:9፤ 26:2፤ 139:1፣23) የሰዎችን ኃጢአት (*ben Adam*)፣ የጻድቃንንና የኃጢአተኞችን። አኪ ሁነቱን ማቴ. 12:36-37፤ 16:27፤ 25:31-46፤ ሐዋ. 10:42፤ ሮሜ. 2:16፤ 14:10፣12፤ 1ጴጥ. 4:5፤ እና ራዕ. 20:11-15 መዝግቦታል። የእግዚአብሔር ፈተና በሁለቱም በጊዜ (ጊዜያዊ) እና ከጊዜ በዘለለ (የፍጻሜ መዳረሻ) ነው። ዘወትርም የዘራነውን በዚህ ዓለም እናጭዳለን፣ እንደዛ ካልሆነ ቀኑ ይመጣል!

## ልዩ ርዕስ፡ እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ ይፈትናል

"ፍተና" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 650፣ ኬቢ. 702፣ ፔይል የተጠናቀቀ) ጥቅም ላይ የዋለው "መሞከር" በሚል ስሜት ነው። እሱ ጥቅም ላይ የሚውለውም አንዱን ወደ ተወሰነ ስፍራ በማምጣት በራሳቸው በተቀመጡት ቅደም ተከተሎች ድርጊቱን ማከናወን ማለት ነው። በግልጽ እንደሚታየው ከዘፍጥረት 12 እስከ 22 እግዚአብሔር አብርሃምን ተከታታይ ወደ ሆኑ ሁኔታዎች አስገብቶታል (ራቢዎች አስር ናቸው ይላሉ)፣ ፍቅርና እምነቱን በእግዚአብሔርና በእግዚአብሔር ላይ ብቻ እንዲያተኩር ለማድረግ። እነዚህ ፈተናዎች ለእግዚአብሔር ሲባል የሚበዙ አይደሉም፤ ነገር ግን ለአብርሃም ሲባልና፣ ስለ እግዚአብሔር ላለው መረዳት፣ እሱም ከከለዳውያን ዑር የጠራው። አብርሃም ቤተሰቡን፣ ቤቱን፣ ባልንጀሮቹን፣ ውርሱን፣ ባህሉን እና የወደፊቱን (የተስፋ ልጁን) እንዲተው ተጠይቋል፣ እግዚአብሔርን በእምነት እንዲከተል። እግዚአብሔር ልጆቹን ሁሉ ቅድሚያ በሚሰጧቸው አካባቢ ይፈትናቸዋል (ማቴ. 4፡1፤ ዕብ. 5:8፤ 12:5-13)።

እግዚአብሔር ይፈትናል (ቢ.ዲ.ቢ. 650) ለማወቅ (ቢ.ዲ.ቢ. 393)። እስራኤላውያን ደጋግመው እግዚአብሔርን ፈትነውታል፣ ባለመታዘዛቸው፣ እናም እሱ ለቃሉ ታማኝ መሆኑን አረጋግጧል። አሁን ደግሞ እግዚአብሔር ለእስራኤልና ለሕዝቦቿ እድል ሰጥቷቸዋል፣ በቃል ሊነገር በማይችል ታማኝነትና እምነት ያሳዩ ዘንድ።

1. እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ በጥቅሉ ይፈትናል
   ሀ. ዘጸ. 15:25፤ 16:4፤ 20:20
   ለ. ዘዳ. 8:2፣16፤ 13:3
   ሐ. መሳ. 2:22፤ 3:1፣4
2. እግዚአብሔር ግለሰብ እስራኤላውያንን ይፈትናል
   ሀ. አብርሃም፣ ዘፍ. 12፡1-12
   ለ. ሕዝቅያስ፣ 2ኛ ዜና. 32፡31
3. የመዝሙር ጸሐፊዎች እግዚአብሔር እንዲፈትናቸው ጮኸዋል፣ አንዳች የተደበቀ እንከን እንዲወገድላቸው (ዝክ. 26:2፤ 139:23)
4. የአኪ የእግዚአብሔር ሰዎች እኩል ተፈትነዋል፣ እንደ ኢየሱስ (ማቴዎስ 4፤ ሉቃስ 4፤ ዕብ. 5፡8)።

## ልዩ ርዕስ፡ በዚያን ቀን

"በዚያን ቀን" ወይም "ያን ቀን" የሚለው ሐረግ ለፍርድ ወይም ለተሐድሶ እግዚአብሔር የሚያደርገውን ጉብኝት ለማመልከት ከ/ክ/ል/በፊት ከ8ኛው መቶ ክፍል ዘመን የነበሩት ነቢያት የነበራቸው አጠቃቀም ነው፡፡

| | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| **ሆሴዕ** | | | | **አሞፅ** | | | | **ሚክያስ** | | |
| **አዎንታዊ** | | **አሉታዊ** | **አዎንታዊ** | **አሉታዊ** | | **አዎንታዊ** | **አሉታዊ** | | | |
| 1:11 | | 1:5 | | | | 1:14 (2) | | | 2:4 | |
| | 2:3 | | | | 2:16 | | | | 3:6 | |
| 2:15 | | | | | | 3:14 | | 4:6 | | |
| 2:16 | | | | | | 3:18(2) | | | | |
| 2:21 | | | | | | 3:20 | | | | 5:10 |
| | 5:9 | | | | 6:3 | | 7:11(2) | | | |
| | 7:5 | | | | 8:3 | | 7:12 | | | |
| | 9:5 | | | | 8:9(2) | | | | | |
| | 10:14 | | | 8:10 | | | | | | |
| | | | 9:11 | | 8:13 | | | | | |

ይህ አይነቱ ሞዴል በተለይ ነቢያት የሚጠቀሙበት ነው፡፡ እግዚአብሔር በጊዜው ለኃጢአት ምላሽን ይሰጣል፤ ነገር ግን ልባቸውንና ክፉ መንገዳቸውን ለሚለውጡ ደግሞ የንስሐና የምህረት እድልም ይሰጣቸዋል የእግዚአብሔርም የመቤዠትና የተሃድሶ ዓላማም ተግባራዊ ይሆናል! እግዚአብሔርም የእርሱን ባህርይ የሚያሣይ ሰዎች አሉት፣ ፍጥረት የተፈጠረበት ዓላማም (የእግዚአብሔርና የሰው ልጆች ያላቸው ህብረት) ይሟላል፡፡

**11፡5 "ነፍሱ ጠልቷል"** ይህ ሰዋዊ ዘይቤ ቋንቋ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 2:4-6። ዘጸ. 15:9፤ ኢሳ. 1:14፤ ኤር. 5:9፣29፤ 6:8፤ 9:9፤ 32:41፤ ሕዝ. 23:18 ተመልከት፣ ለተመሳሳይ የ*ኔፊሽ* አጠቃቀም (ቢ.ዲ.ቢ. 659፣ see note at መዝ. 3:2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)።

ይህ ቁጥር ሊመለከት የሚችለው ክፉውን ብቻ ነው፣ "ጻድቅ" የሚለው የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው (መዝ. 11፡3ለ)። እንደዚያ ከሆነ፣ ያህዌ እና "ጻድቁ" ተያያዥ ናቸው (ዝክ. 11፡3ለ፣ 7ሀ)።

ብኪ እግዚአብሔር የሚጠላቸውን በርካታ ነገሮች ይዘረዝራል።

1. አመንዝራነት (ጣዖት አምልኮ) – ዘዳ. 12:31፤ 16:22፤ ኤር. 44:4፤ ሆሴ. 9:15
2. ኃጢአት የሚሠሩትን ሁሉ – መዝ. 5:5
3. ዓመጻ የሚወደውን – መዝ. 11:5

4-9. ዝርዝሩን ተመልከት ምሳ. 6:10-19 ላይ (ደግሞም ዘካ. 8:16-17 ላይ ያለውን ማስታወሻ)

10. የእስራኤል ሐሰተኛ፣ አሳፋሪ አምልኮ – ኢሳ. 1:14፤ አሞጽ 5:1፤ 6:8
11. መፋታትን – ሚል. 2:16

**11፡6**
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**
**አየተመት፣ አኢመቅ፣**
**LXX** **"ያዘንባል"**
**አእት Bible** **"እግዚአብሔር ያዘንባል"**

*ግሡ* (ቢዲቢ 565፣ ኬቢ 574) ተጽዕኗዊ ነው፣ አእት መጽሐፍ ቅዱስ እና መልኅቅ መጽሐፍ ቅዱስ በትክክል ይተረጉሙታል፣ ነገር ግን ሌሎች ትርጉሞች በቅርጹ ተጽዕኗዊ እንደሆነ ይገምታሉ፣ በፍችው ሳይሆን።

**▣**
**አአመመቅ፣ ኤምቲ፣**
**LXX** **"ወጥመድ"**
**አአመመቅ ኅዳግ** **"እሳትና ዲን"**
**አኪጀት፣ አየተመት፣**
**አእቅ፣ አኢመቅ፣**
**ጄፒኤስኦኤ** **"ዲን"**

*ዐውደ-ጽሑፉ* ከ "ወጥመድ" ማረሚያ የሚሻ ይመስላል פחים (ቢዲቢ 809) ወደ "ዲን" פחם (ቢዲቢ 809)። የዩቢኤስ የጽሑፍ ማሳያ ለ "ወጥመድ" የ "ለ" ደረጃ ይሰጣል።

**11፡6ለ** ይህ የሚጠቅሰው
1. ግነታዊ ቅኔአዊ ምስያ ስለዚህ ሕይወት ሁኔታ
2. የፍርድን እውነታነት ከሕይወት በኋላ (ዘዳ. 32፡22)

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው? መዝ. 1፡6 ላይ።

**▣ "እሳት"** ይህ ተደጋጋሚ ዘይቤ ነው፣ የፍርድና የማንጻት።

## ልዩ ርዕስ፡ እሳት (ቢዲቢ 77)

እሳት ሁለቱንም፣ አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ ፍችዎች አሉት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ።

ሀ. አዎንታዊ/Positive
1. ያሞቃል (ኢሳ. 44:15፤ ዮሐንስ 18:18)
2. ብርሃን (ኢሳ.50:11፤ ማቴ. 25:1-13)
3. ያበስላል (ዘጸ. 12:8፤ ኢሳ. 44:15-16፤ ዮሐንስ 21:9)
4. ያጠራል (ዘኍ. 31:22-23፤ ምሳ. 17:3፤ ኢሳ. 1:25፤ 6:6-8፤ ኤር. 6:29፤ ሚል. 3:2-3)
5. ቅድስና (ዘፍ. 15:17፤ ዘጸ. 3:2፤ 19:18፤ ሕዝ. 1:27፤ ዕብ. 12:29)
6. የእግዚአብሔር አመራር(ዘጸ. 13:21፤ ዘኍ. 14:14፤ 1 ነገሥ. 18:24)
7. የእግዚአብሔር ኃይል ማስታጠቅ (ሐዋ. 2:3)
8. ጥበቃ (ዘካ 2፡5)

ለ. አሉታዊ / Negative
1. ያቃጥላል (ኢያ.6:24፤ 8:8፤ 11:11፤ ማቴ. 22:7)
2. ያጠፋል (ዘፍ. 19:24፤ ሌዋ. 10:1-2)
3. ቁጣ (ዘኍ. 21:28፤ ኢሳ. 10:16፤ ዘካ. 12:6)
4. ቅጣት (ዘፍ. 38:24፤ ሌዋ. 20:14፤ 21:9፤ ኢያ. 7:15)
5. የተሳሳተ መናፍስትነት ምልክት (የፍጻሜ) (ራዕ. 13:13)

ሐ. የእግዚአብሔር ቁጣ በኃጢአት ላይ የሚገለጠው በእሳት ዘይቤዎች ነው
1. የእሱ ቁጣ ይነዳል (ሆሴ. 8፡5፤ ሶፎ. 3፡8)
2. እሱም እሳትን ያወጣል (ነሀ. 1፡6)
3. ዘላለማዊ እሳት (ኤር. 15:14፤ 17:4)
4. የመጨረሻው ፍርድ (ማቴ. 3:10፤ 13:40፤ ዮሐንስ 15:6፤ II ተሰ. 1:7፤ II ጴጥ. 3:7-10፤ ራዕ. 8:7፤ 16:8)

መ. በመጽሐፍ ቅዱስ እንዳሉ በርካታ ዘይቤዎች (ማለትም፣ እርሾ፣ አንበሳ) እሳትም በረከት ወይም መርገም ሊሆን ይችላል፣ በዐውደ ጽሑፉ ላይ በመመሥረት ፡፡

▣
**አአመመቅ፣ አኪጀት** **“የሚያቃጥል ነፋስ”**
**አየተመት፣ አእቅ፣**
**አኢመቅ፣ ጀፒኤስአኤ፣**
**የተእመቅ** **“የሚያቃጥል ነፋስ”**
**LXX** **“አውሎ ነፋስ”**
**አእት** **“አውሎ ነፋስ”**

ይህ የአልፎ አልፎ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 273) በመሠረቱ የሚለው “ሙቀት” ነው። ጥቅም ላይ የዋለውም

1. መዝሙር 11:6 — ነፋስን የሚገልጽ
2. መዝሙር 119፡53 — እንደሚነድ ቁጣ
3. ሰቆቃወ 5፡10 — እንደ ጽኑ ራብ

ትርጓሜያዊ ጥያቄ የሚሆነው፣ “ይህ ቃል ተለጣጣቂዎቹን ስሞች ይቀጥላልን (ቢ.ዲ.ቢ. 809፣ 77፣ 172፣ ኢዮብ 1:16) ወይስ አዲስ ዘይቤ ይጀምራል?” የሚል ነው።

1. አጥፊ አውሎ ነፋስ (መዝ. 58:9፤ ምሳ. 1:27፤ ሆሴ. 8:7፤ አሞጽ 1:14፤ ናሆ. 1:3)
2. ሙቅ የበረሀ ነፋስ (መዝ. 90:56፤ 103:15-16)

▣ **“ጽዋቸው”** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ለሰው ዕጣ ፈንታ፣ ዘወትርም አሉታዊ (መዝ. 75፡8፣ ነገር ግን አንዳንዴ አዎንታዊ ይሆናል፣ መዝ. 16፡5)። እሱም ከጠጭነት ጋር ይያያዛል (ኢሳ. 51:17፤ ኤር. 25:15)።

ይኸው ተመሳሳይ ፈሊጥ በኢየሱስ ጥቅም ላይ ውሏል

1. ማቴ. 20:22፤ ማርቆስ 10:38፣39
2. ማቴ. 26:39፣42፤ ማርቆስ 14:36፤ ሉቃስ 22:42
3. ዮሐንስ 18:11

**11:7** ያህዌ በባሕርዩ ጻድቅ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:5 ላይ፣ ዘጸ. 9:27፤ ዕዝራ 9:15፤ ነህ. 9:8፤ መዝ. 119:137፤ ኤር. 12:1፤ ሰቆ. 1:18፤ ዮሐንስ 17:25፤ ራዕ. 16:5፣7)።

አንዳንዶቹ የጻድቁ አምላክ ድርጊቶች:

1. የሰዎችን ልብ ይፈትናል – መዝ፣ 7:9፤ 11:5፤ ኤር. 20:12
2. በጽድቅ ይፈርዳል – መዝ. 7:11
3. ጽድቅን ይወዳል – መዝ. 11:7፤ 33:5፤ 146:8
4. ደግ እና ጻድቅ ነው – መዝ. 116:5
5. የክፉዎችን አንገታቸውን ይቆርጣል – መዝ. 129:4
6. ጻድቅ ነው፣ በመንገዱ ሁሉ – መዝ. 145:7፤ ዳን. 9:14

**11:7ለ “ቅንነት ግን ፊቱን ታየዋለች።”** አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ይህ የኢየሱስ ቃል ምንጭ ከሆነ፣ ማቴ. 5:8 ላይ። እግዚአብሔር ጻድቅ ነው (ሌዋ. 19:2፤ ማቴ. 5:48)። ማንም እግዚአብሔርን አይቶ በሕይወት የሚኖር የለም (ማለትም፣ ዘጸ. 33:11፣17-23)፣ ሆኖም እነርሱ በእሱ/ኢየሱስ ጻድቅ የሆኑ ከመለኮት ጋር የቀረበ ወዳጅነት ይኖራቸዋል (ኢዮብ 19:25-27፤ 27:4፤ መዝ. 17:15፤ ማቴ. 5:8፤ 1 ዮሐንስ 3:2)!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. “ሸሸ” ምን ማለት ነው?
2. ቁጥር 3ን በራስህ ቋንቋ አብራራ።
3. ከቁጥር 4፣ ያህዌ የት ነው፣ ሰማይ ወይ መቅደስ?
4. ያህዌ ሰዎችን ይፈትናልን (ቁ. 5) ?
   እንዴትና ለምን?

## መዝሙር 12
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር በክፉዎችን ተቃውሞ ረድኤት ነው | የሰው ክፋትና የእግዚአብሔር ቋሚነት | ከግላዊ ጠላቶች ለማምለጥ ጸሎት (ሰቆቃ) | የዕርዳታ ጸሎት | ክፉውን ዓለም በመቃወም |
| <u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>"ለመዘምራን አለቃ፤ ስምንት አውታር ባለው በገና። የዳዊት መዝሙር" | | | | 12:1-2 |
| 12:1-5 | 12:1-2 | 12:1-2 | 12:1-2 | 12:3-5 |
| | 12:3-5 | 12:3-4 | 12:3-4 | |
| | | 12:5-6 | 12:5 | 12:6 |
| 12:6-8 | 12:6-7 | | 12:6 | 12:7-8 |
| | | 12:7-8 | 12:7-8 | |
| | 12:8 | | | |

### **የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 12፡1-5**

**1አቤቱ፥ አድነኝ ደግ ሰው አልቆአልና፥**
**ከሰው ልጆችም መተማመን ጐድሎአልና።**
**2እርስ በርሳቸው ከንቱ ነገርን ይናገራሉ**
**በሽንገላ ከንፈር ሁለት ልብ ሆነው ይናገራሉ።**
**3የሽንገላን ከንፈሮች ሁሉ እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል፥**
**ታላቅ ነገርን የምትናገረውን ምላስ**
**4ምላሳችንን እናበረታለን ከንፈራችን የእኛ ነው፥**
**ጌታችን ማን ነው? የሚሉትን።**
**5ስለ ድሆች መከራ፥ ስለ ችግረኞች ጩኸት እግዚአብሔር፦**
**አሁን እነሣለሁ ይላል መድኃኒትን አደርጋለሁ፥ በላዩም እገልጣለሁ።**

**12፡1 "አድነኝ፣ ጌታ"** እንዴት ያለው ጽኑ የርዳታ ጩኸት ነው (ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*)። በብኪ ይህ ቃል የአካላዊ ትድግና አንድምታ አለው፣ ነገር ግን በአኪ የሚወስደው አጽንዖት መንፈሳዊ ደኅንነትን ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት በብኪ፣ መዝ. 13፡5-6 ላይ።

ዘወትር የማስበው አንዱ አካላዊ ትድግናን ማግኘቱ አሳዛኝ መሆኑን ነው (ማለትም፣ ጤና፣ ጦርነት፣ ገንዘብ ነክ) ነገር ግን የመንፈሳዊ ትድግናን ደስታና ጥቅም ካጣ! በአኪ ፈውስ ዘወትር መንፈሳዊ መለወጥን አያመጣም። ሰዎች እጅግ የሚያስፈልጋቸው እግዚአብሔር ነው፣ የሁኔታዎች መለወጥ ሳይሆን!

◘ **"ደግ ሰው አልቆአልና፥"** በስንኝ 1 እና በስንኝ 2 መካከል ያለውን ትይዩነት ተገንዘብ። እነዚህ ሁለቱም የሚናገሩት የታማኝ ተከታዮችን ሞት ነው። ይህ የተጠቃለለ ሰቆቃ ነው፣ ምንም እንኳ LXX "እኔን" ቢኖርበትም፣ 12፡1-2 ላይ።
ለ "ታማኝ" (ቢዲቢ 52 I) ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ እና ታማኝነት በብሉይ ኪዳን (אמן)

I. የመክፈቻ መግለጫ

የዚህን ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ አጠቃቀም መቀመጥ የሚኖርበት፣ ለአዲስ ኪዳን በጣም ወሳኝ እንደሆነ ነው፣ በብኪ በግልጽ እንደ ተቀመጠው ሳይሆን። እሱ በርግጥ እዚያ ነው፣ ነገር ግን የተገለጠው በተመረጡ ቁልፍ አንቀጾችና ሰዎች ነው።
ብኪ የሚቀይጠው

- ሀ. ግለሰብን እና ማኅበረሰቡን
- ለ. የግለሰብን ገጠመኝ እና ኪዳናዊ መታዘዝን

  እምነት ግለሰባዊ ገጠመኝና የየቀኑ የአኗኗር ስልት ነው! እሱም በግለሰብ ማስረዳት ይቀላል፣ በቃላታዊ መልኩ ከመግለጽ ይልቅ (ማለት፣ የቃላት ጥናት)። ይህ ግለሰባዊ ገጽታ በተሻለ የተገለጠው
  - ሀ. አብርሃምና ዘሩ
  - ለ. ዳዊትና እስራኤል

እነዚህ ሰዎች የተገናኙት/ያጋጠማቸው እግዚአብሔር ነው እንዲሁም ሕይወታቸው በቋሚነት ተለውጧል (የፍጽምና ሕይወት አይደለም፣ ግን ቀጣይነት ያለው እምነት)። ፈተና የእምነታቸውን ድካምና ጥንካሬ ይገልጣል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት፣ ግን ጓደኛዊ፣ መተማመን ያለበት ግንኙነት በጊዜ ሁሉ ይቀጥላል! እሱም ተፈትኗል ጠርቷልም፣ ግን እሱ ይቀጥላል እንደ መሰጠታቸውና የሕይወት ስልታቸው ማስረጃ።

II. ዋናው ሥርወ ቃል አጠቃቀሙ

- ሀ. אמן (ቢዲቢ 52)
  1. ግሥ VERB
     - ሀ. *Qal* stem ግንድ — ለመደገፍ፣ ለመንከባከብ (ማለትም፣ 2ኛ ነገሥ. 10:1፣5፤ አስቴር 2:7፣ ሥነ-መለኮታዊ ያልሆነ አጠቃቀም)
     - ለ. *Niphal* stem ኒፋል ግንድ — ርግጠኛ ለመሆን ወይም ለማጽናት፣ ለማቆም፣ ለማረጋገጥ፣ ታማኝ ለመሆን ወይም የሚታመኑት
       - (1) ለሰዎች፣ ኢሳ. 8:2፤ 53:1፤ ኤር. 40፤14
       - (2) ለነገሮች፣ ኢሳ. 22፡23
       - (3) ለእግዚአብሔር፣ ዘዳ. 7:9፣12፤ ኢሳ. 49:7፤ ኤር. 42:5
     - ሐ. *Hiphil* stem ሂፊል ግንድ — ጸንቶ መቆም፣ ማመን፣ መታመን
       - (1) አብርሃምም እግዚአብሔርን አመነ፣ ዘፍ. 15፡6
       - (2) እስራኤላውያን በግብፅ አመኑ፣ ዘጸ. 4:31፤ 14:31 (ከዘዳ. 1:32 የሚቃረን)
       - (3) እስራኤላውያን ያህዌን አመኑ፣ በሙሴ በኩል የተናገራቸውን፣ ዘጸ. 19:9፤ መዝ. 106:12፣24
       - (4) አካዝ በእግዚአብሔር አላመነም፣ ኢሳ. 7፡9
       - (5) በእሱ የሚያምን ሁሉ፣ ኢሳ. 28፡16
       - (6) ስለ እግዚአብሔር የሚታመኑ ሐቆች፣ ኢሳ. 43፡10-12
  2. ስም (ተባዕታይ) — ታማኝነት (ማለትም፣ ዘዳ. 32:20፤ ኢሳ. 25:1፤ 26:2)
  3. ተውሳከ ግሥ — በእውነቱ፣ በጣሙን፣ እስማማለሁ፣ እንዲህ ሊሆን ይችላል (ዘዳ.27:15-26፤ 1 ነገሥ. 1:36፤ 1 ዜና. 16:36፤ ኢሳ. 65:16፤ ኤር. 11:5፤ 28:6)። ይህ የ "አሜን" የኅብረት አምልኳዊ አጠቃቀም ነው፣ በብኪ እና በአኪ።
- ለ. (תמא (ቢዲቢ 54) አንስታይ ስም፣ ጽናት፣ ታማኝነት፣ እውነት
  1. ለሰዎች፣ ኢሳ. 10:20፤ 42:3፤ 48:1
  2. ለእግዚአብሔር፣ ዘጸ. 34:6፤ መዝ. 117:2፤ ኢሳ. 38:18፣19፤ 61:8
  3. ለእውነት፣ ዘዳ. 32:4፤ 1 ነገሥ. 22:16፤ መዝ. 33:4፤ 98:3፤ 100:5፤ 119:30፤ ኤር. 9:4፤ ዘካ. 8:16
- ሐ. הנומא (ቢዲቢ 53)፣ ጽናት፣ ጽኑዕነት፣ አማኝነት
  1. ለእጆች፣ ዘጸ. 17፡12
  2. ለጊዜ፣ ኢሳ. 33፡6
  3. ለሰዎች፣ ኤር.5:3፤ 7:28፤ 9:2
  4. ለእግዚአብሔር፣ መዝ. 40:11፤ 88:12፤ 89:2፣3፣6፣9፤ 119:138

III. የጳውሎስ የብኪ ጽንሰ-ሐሳብ አጠቃቀም rma

ሀ. ጳውሎስ የያህዌንም ሆነ የብኪ አዲሱን መረዳቱን መሠረት ያደረገው በራሱ ግላዊ ድንገተኛ ግንኙነት ነው፣ ከኢየሱስ ጋር በደማስቆ መንገድ (ሐዋ. 9፤ 22፤ 26)።

ለ. እሱም የብኪን ድጋፍ ፈልጓል ለአዲሱ መረዳቱ በሁለት የብኪ ቁልፍ አንቀጾች ላይ፣ እነሱም ሥርን የሚጠቀሙ

1. ዘፍ. 15፡6 — የአብራም ግለሰባዊ ግንኙነቱ የተነሣሣው በእግዚአብሔር ነው (ዘፍጥረት 12) ውጤቱም በእምነት የመታዘዝ ሕይወት የሆነ (ዘፍጥረት 12-22)። ጳውሎስ ይሄንን በሮሜ 4 እና ገላትያ 3 ላይ ጠቅሶታል።

2. ኢሳ. 28፡16 — በእሱ የሚያምኑ ሁሉ (ማለትም፣ እግዚአብሔር የፈተነው እና ያስቀመጠው የማዕዘን ድንጋይ) ፈጽሞ
   ሀ. ሮሜ 9፡33፣ "አያፍርም" ወይም "ቅር አይሰኝም"
   ለ. ሮሜ 10፡11፣ እንደ ላይኛው የሆነ
3. ዕንባ. 2፡4 — እነሱ ታማኙን እግዚአብሔርን የሚያውቁ የመታመን ሕይወት መኖር ይኖርባቸዋል (ኤር. 7፡28)።

ጳውሎስ ይሄንን ጽሑፍ በሮሜ 1፡17 እና ገላ. 3፡11 (ዕብ. 10፡38 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)።

IV. የጴጥሮስ የብሉይ ኪዳንን ጽንሰ ሐሳብ አጠቃቀም
   ሀ. ጴጥሮስ የደባለቀው
      1. ኢሳ. 8:14 – 1 ጴጥ. 2:8 (የማሰናከያ ድንጋይ)
      2. ኢሳ. 28:16 – 1 ጴጥ. 2:6 (የማዕዘን ድንጋይ)
      3. መዝ. 111፡22– 1 ጴጥ. 2:7 (የተናቀ ድንጋይ)
   ለ. እስራኤልን የሚገልጸውን የተለየ ቋንቋ ገለበጠው፣ "የተመረጠ ዘር፣ የንጉሥ ክህነት፣ ቅዱስ ሕዝብ፣ ለእግዚአብሔር ርስት የሆነ ሕዝብ"
      ሀ. ዘዳ.10:15፤ ኢሳ. 43:21
      ለ. ኢሳ. 61:6፤ 66:21
      ሐ. ዘጸ. 19:6፤ ዘዳ. 7:6
      እና አሁን የተጠቀመው በክርስቶስ ባለ የቤተ-ክርስቲያን እምነት ነው
V. የዮሐንስ የጽንሰ-ሐሳቡ አጠቃቀም
   ሀ. የእሱ የአዲስ ኪዳን አጠቃቀም
      "አመነ" የሚለው ቃል ከግሪክ ቃል (*pisteuō*) ሲሆን፣ እሱም ደግሞ የሚተረጎመው "ማመን፣" "እምነት፣" ወይም "መታመን" በሚል ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ስሙ በዮሐንስ ወንጌል ላይ አልተከሰተም፣ ግሡ ግን ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል። በዮሐንስ 2፡23-25 የሕዝቡ ቅንነት የተሞላው መሰጠት መኖሩ ርግጠኛ አይደለም፣ የናዝሬቱን ኢየሱስ እንደ መሲሕ ለመቀበል። ሌለኛው ምሳሌ፣ የዚህ ቃል "ማመን" ጥራዝ ነጠቃዊ አጠቃቀም የሚገኘው በዮሐንስ 8፡31-59 እና ሐዋ. 8:13፣ 18-24. ላይ ነው። እውነተኛው የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ከመነሻው ምላሽ ላቅ ይላል። እሱም መከተል ያለበት ወደ ደቀመዝሙራዊ ሂደት ነው (ማቴ. 13:20-22፣31-32)።
   ለ. የእሱ አጠቃቀም ከመስተፃምር ጋር
      1. *eis* ማለት "ወደ... ውስጥ (በ)" ማለት ነው። ይህ የተለየ ዓይነት አወቃቀር አጽንዖት የሚሰጠው አማኞች እምነታቸውን/መታመናቸውን ማድረግ ያለባቸው በኢየሱስ ላይ ነው
         ሀ. በስሙ (ዮሐንስ 1:12፤ 2:23፤ 3:18፤ 1 ዮሐንስ 5:13)
         ለ. በእሱ (ዮሐንስ 2:11፤ 3:15፣18፤ 4:39፤ 6:40፤ 7:5፣31፣39፣48፤ 8:30፤ 9:36፤ 10:42፤ 11:45፣ 48፤ 17:37፣42፤ ማቴ. 18:6፤ ሐዋ 10:43፤ ፊሊጵ. 1:29፤ 1 ጴጥ. 1:8)
         ሐ. በእኔ (ዮሐንስ 6:35፤ 7:38፤ 11:25፣26፤ 12:44፣46፤ 14:1፣12፤ 16:9፤ 17:20)
         መ. በልጁ (ዮሐንስ 3:36፤ 9:35፤ 1 ዮሐንስ 5:10)
         ሠ. በኢየሱስ (ዮሐንስ 12:11፤ ሐዋ. 19:4፤ ገላ. 2:16)
         ረ. በብርሃኑ (ዮሐንስ 12፡36)
         ሰ. በእግዚአብሔር (የሐንስ 14:1)
      2. *en* ኢን ማለት "ውስጥ" ነው፣ እንደ ዮሐንስ 3:15፤ ማርቆስ 1:15፤ ሐዋ. 5:14
      3. *epi* ኢፒ ማለት "ውስጥ" ወይም "በላይ፣" ነው፣ እንደ ማቴ. 27:42፤ ሐዋ. 9:42፤ 11:17፤ 16:31፤ 22:19፤ ሮሜ. 4:5፣ 24፤ 9:33፤ 10:11፤ 1 ጢሞ. 1:16፤ 1 ጴጥ. 2:6
      4. ቀጥተኛ ያልሆነ የግሥ ተሳቢ፣ ያለ መስተጻምር እንደ ገላ. 3:6፤ ሐዋ. 18:8 27:25፤ 1 ዮሐንስ 3:23፤ 5:10
      5. *hoti* ሆቲ፣ ፍችውም "ያመነው" ምን እንዳመነ ይዘቱን ያመለክታል
         ሀ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ቅዱሱ መሆኑን (ዮሐንስ 6፡69)
         ለ. ኢየሱስ ያለና የሚኖር ነው (ዮሐንስ 8፡24)
         ሐ. ኢየሱስ በአብ አለ፣ አብም በእሱ አለ (ዮሐንስ 10፡38)
         መ. ኢየሱስ መሲሕ ነው (ዮሐንስ 11:27፤ 20:31)
         ሠ. ኢየሱስ የእግዚአብሔር ልጅ ነው (ዮሐንስ 11:27፤ 20:31)
         ረ. ኢየሱስ የተላከው በአብ ነው (ዮሐንስ 11፡42፤ 17፡8፣21)
         ሰ. ኢየሱስ ከአብ ጋር ያለው ነው (ዮሐንስ 14፡10-11)
         ሸ. ኢየሱስ ከአብ የመጣው ነው (ዮሐንስ 16፡27፣30)
         ቀ. ኢየሱስ ራሱን በአብ የኪዳን ስም፣ "እኔ ነኝ" በሚል ገልጿል (ዮሐንስ 8፡24፤ 13፡19)
         በ. እኛም ከእሱ ጋር እንኖራለን (ሮሜ 6፡8)

ተ. ኢየሱስ ሞቶ ዳግም ተነሥቷል (1ኛ ተሰ. 4፡14)

VI. *መደምደሚያ*

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ለመለኮታዊ ቃል/ተስፋ የሰዎች ምላሽ ነው። እግዚአብሔር ዘወትር መነሻውን ይወስዳል (ማለትም፣ ዮሐንስ 6፡44፣ 65)፣ ነገር ግን የዚህ መለኮታዊ ግንኙነት ክፋይ ለሰዎች ምላሽ ተትቷል።*

*ሀ. ማመን*

ለ. ኪዳናዊ *መታዘዝ*

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት*

1. *ግለሰባዊ ግንኙነት ነው (መነሻ እምነት)*
2. *የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት መተማመኛ ነው (በእግዚአብሔር መገለጥ ማመን)*
3. *ለእሱም ምላሽ በሚሆን ተገቢ ምላሽ (የየዕለቱ እምነት)*

*መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ለመንግሥተ ሰማያት ትኬት አይደለም ወይም የኢንሹራንስ ፖሊሲ። እሱ ግለሰባዊ ግንኙነት ነው። ይህ የፍጥረት እና የሰው ልጆች ዓላማ ነው፣ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል ለተፈጠሩት (ዘፍ. 1፡26-27)። ፍሬ ነገሩ "መቀራረብ" ነው። እግዚአብሔር ኅብረትን ይሻል፣ የሆነ ሥነ-መለኮታዊ አቋም ሳይሆን! ነገር ግን ከቅዱሱ እግዚአብሔር ጋር የሚሆን ኅብረት፣ ልጆች "የቤተሰባቸውን" ባሕርይ እንደሚያንጸባርቁት ያለውን ይጠይቃል (ማለትም፣ ቅድስና፣ ሌዋ. 19፡2፤ ማቴ. 5፡48፤ 1 ጴጥ. 1፡15-16)። ውድቀት (ዘፍጥረት 3) ተገቢውን ምላሽ የመስጠት ችሎታችንን ጎዳው። ስለሆነም፣ እግዚአብሔር በእኛ ፈንታ አደረገ (ሕዝ. 36፡27-38)፣ "አዲስን ልብ" በመስጠት፣ እንዲሁም "አዲስ መንፈስ፣" እሱም በእምነት እና ንስሐ በመግባት በኩል ከእሱ ጋር ኅብረት እንዲኖረንና እንድንታዘዘው የሚያስችለንን!*

*እነዚህ ሦስቱም ዋነኞች ናቸው። ሦስቱም ሁሉ መጠበቅ ይኖርባቸዋል። ግቡም እግዚብሔርን ለማወቅ ነው (በዕብራውያንና በግሪክ አግባቦች) እንዲሁም በሕይወታችን የእሱን ባሕርይ ማንጸባረቅ። የእምነት ግብ አንድ ቀን የሚገኝ መንግሥተ ሰማይ አይደለም፣ ነገር ግን በእየቀኑ ክርስቶስን መምሰል ነው!*

*የሰዎች ታማኝነት ውጤቱ ነው (አኪ)፣ መሠረቱ ሳይሆን (ብኪ) ከእግዚብሔር ጋር ላለ ግንኙነት፡ የሰዎች እምነት በእሱ ታማኝነት፤ የሰዎች መታመን በአሱየታ መነ መሆን ላይ። አንኳሩ የአዲስ ኪዳን አመለካከት በደኅንነት ላይ የሚሆነው፣ ሰዎች የግድ ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል ከመነሻውም ሆነ በቀጣይነት፣ መነሻ ለሆነው ጸጋ እና የእግዚአብሔር ምሕረት፣ በክርስቶስ ለተገለጠው። እሱ ወዷል፣ እሱ ልኳል፣ እሱ ሰጥቷል፤ እኛም በእምነትና በታማኝነት ምላሹን ልንሰጥ ይገባል (ኤፌ. 2፡8-9 እና 10)!*

*ታማኙ እግዚአብሔር ታማኝ የሆነ ሕዝብ ይሻል፣ ራሱን ለእምነት ቢሱ ዓለም ለመግለጽና በእሱ ላይ ለሚሆን ግላዊ እምነት ለማምጣት።*

◘

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

**አየተመት "ጠፍቷል"**

**LXX፣ አኢመቅ፣**

**ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ "አልቋል"**

ስንኝ አንድ ላይ የሚገኘው "ማለቅ" ከዚህ ቃል ጋር ትይዩ ነው (ቢዲቢ 821 II)፣ እሱም ብኪ ላይ እዚህጋ ብቻ የሚገኝ። አንዳንዶች የሚሉት የተለየ ሥር ነው (ቢዲቢ 67) እሱም ኢሳ. 16፡4 ላይ የሚገኝ።

የዩቢኤስ የጽሑፍ አመላካች (ገጽ 177) ሁለት መንገዶችን ይጠቁማል፣ ይሄንን ግሥ ለመረዳት።

1. ቁጥራቸው በብዛት ቀንሷል (LXX)
2. ሙሉ ለሙሉ ጠፍተዋል (ዝኪ. ቁ. 1ሀ እና ቁ. 3ሀ)

**12፡2-4** "የመናገርን" ጭብጥ ተገንዘብ (ማለትም፣ ከንፈሮች፣ ምላስ)። የሁለት ልብ ሰው የስሕተት መልእክት በያህዌ እውነተኛ መገለጥ ተቃርኗል (መዝ. 12፡6)።

በየዕለቱ አማኞች የትኛው መልእክት እውነት/ሀሰት እንደሆነ ማስረገጥ ይኖርባቸዋል፤ ከወደቀው ሰው/ከእግዚአብሔር (ዘዳ. 13፡1-5፤ 18፡14-22፤ ማቴዎስ 7፤ 1 ዮሐንስ 4፡1-3)!

**12፡2 "ከንቱ ነገርን ይናገራሉ"** ይህ በጥሬው "ባዶነት" ወይም "ከንቱነት" ነው (ቢዲቢ 996)። "የንግግር ባዶነት" ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (መዝ. 41፡6፤ 144፡8፣11፤ ምሳ. 30፡9፤ ኢሳ. 59፡4፤ ሕዝ. 13፡8-9፤ ሆሴ. 10፡4)።

በአንዳንድ ዐውደ-ጽሑፎች ለሐሰት ምስክርነት ጥቅም ላይ ውሏል (ዘጸ. 20፡16፤ 23፡1፤ ዘዳ. 5፡20) በፍርድ ቤት። በሌሎች ቦታዎች እሱ የሚያመለክተው ሐሰተኛ ትንቢቶችን ነው (ሰቆ. 2፡14፤ ሕዝ. 22፡28፤ ዘካ. 10፡2)።

አንድ ነገር ርግጠኛ ነው፣ ይህ ቃል ባሕርይ የሚያደርገው ሐሰት ተከታዮችን ነው! አፋቸው መንታ ልባቸውን ይገልጣል (ዝኪ. ቁ. 2፤ ማቴ. 12፡34፤ 15፡18፤ ማርቆስ 7፡20-23፤ ሉቃስ 6፡45፤ ያዕቆብ 3፡2-12)።

**12፡3** ዘማሪው ለያህዌ ጥሪ የሚያደርገው ዝም እንዲያሰኝ ነው ("እንዲቆርጥ" – ቢዲቢ 503፣ ኬቢ 500፣ *ሂፊል ተጽዕኖዊ*)

1. የሽንገላ አንደበት ("ለስላሳ አንደበት፣" መዝ. 5፡9)
2. ታላቅን ነገር የሚናገር አንደበት

**12፡4** ይህ ቁጥር የሚያመለክተው "የመንታ ልብን" እውነተኛ ልብ ነው ("ልብ እና ልብ")። ይህ ሰው ለያህዌ የማይፈቅድ ነው፣ ሕይወቱን ያህዌ እንዲቆጣጠረው! ይህ የወደቀው ሰው አዝማሚያ ዋነኛ ነጥብ ነው።

▣ **"የሚሉት"** አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ. 751) የሚያሳስበን መዝሙረኛው ዘወትር የሚጠቅሰው ወይም የሚያነሣው የክፉውን ሐሰተኛ ቃላት ነው (መዝ. 3:2 እና 10:11፤ ደግሞም 2 ጴጥ. 3:1-4፤ ይሁዳ ቁ. 18-19 ተመልከት)።

**12:5** ያህዌ ለምን "እንደሚነሣ" ይገልጻል (ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 3:7 ላይ)።

1. በችግረኛው መጥፋት ሳቢያ
2. በችግረኛው ጩኸት ሳቢያ (ቢዲቢ 60 I)

ያህዌ በሕዝቡ ጸሎትና ሁኔታ ይነካል (ማለትም፣ ዘጸ. 3:7፤ 2:25፤ ነህ. 9:9፤ ኢሳ. 63:9፤ ሐዋ. 7:34)። ያህዌ (ከጣዖታት በተለየ መልኩ የሚሰማ፣ የሚያይ፣ እና የሚሠራ አምላክ ነው!

▣ **"ደኅንነት"** ይህ ስም "ርዳታ" ከሚለው ግሥ ነው (ቢዲቢ 446 ኬቢ 448) ቁጥር 1 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል። እሱም ከዓረብኛ ሥር ተመሳሳይ ይመስላል፣ እሱም ሰፊ ወይም የሰፋ ዳርቻን ይጠቅሳል (መዝ. 4:1፤ 31:8፤ 118:5)። ይኸም "የጠባብ" ወይም "የታመቀ" ተቃራኒ ፈሊጥ ነው።

▣ **"ይናፍቃል"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 806፣ ኬቢ 916፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ) በመሠረቱ ፍችው "መተንፈስ" ወይም "ትንፋሽን ማውጣት" ነው።

1. ለያህዌ ጥቅም ላይ ውሏል ለያህዌ ላለመውደዱ መግለጫ — መዝ. 10፡5
2. በፍርድ ቤት ለሚደረግ ምስክርነት ጥቅም ላይ ውሏል – ምሳ. 6:19፤ 12:17፤ 14:5፣25፤ 19:5፣9
3. በቀኑ ቀዝቃዛ ክፍል – ማኅልየ ማኅልይ 2:17፤ 4:6
4. አንድን ነገር ለመናፈቅ ወይም ለመሻት ጥቀም ላየ ውሏል
   ሀ. የደኅንነት ስፍራ — መዝ. 12፡5
   ለ. ለሚፈጸም ራዕይ — ዕን. 2፡3

LXX ይሄንን ስንኝ ቅኔ የሚተረጉመው ያህዌ እንደሚናገረው ነው፣ "በደኅና አኖራለሁ፤ እሱን ተቃውሜ በነጻነት እናገራለሁ። ጄፒኤስኦኤ "ርዳታን እሰጣለሁ፣ እሱ ያጸናዋል" የሚል አለው።

---

**መዝሙር ፡ 12፡6-8**

**[6]በምድር ላይ እንደ ተፈተነ ሰባት ጊዜ እንደ ተጣራ ብር።**
**የእግዚአብሔር ቃላት የነጹ ቃላት ናቸው።**
**[7]አቤቱ፥ አንተ ጠብቀን፥**
**ከዚህችም ትውልድ ለዘላለም ታደገን።**
**[8]በሰው ልጆች ዘንድ ምናምንቴ ከፍ ከፍ ባለ ጊዜ**
**ክፉዎች በዙሪያው ሁሉ ይመላለሳሉ።**

---

**12፡6-8** የያህዌን መገለጥ ከክፉው ረብ-የለሽ አዝማሚያ ጋር በተቃርኖ ያሳያል። የያህዌ መልእክት ባሕርዩ

1. ንጹሕ ቃላት (መዝ. 19:8፤ 119:140)
2. የጠራ ብር (መዝ. 18:30፤ ምሳ. 30:5)

እሱ ለቃሉ ታማኝ ነው (ዝኪ. ቁ. 7)። ክፉዎች ራሳቸውን የሚገልጡት በቃላቸውና በግብራቸው ነው (ዝኪ. ማቴ. 7:15-23፣24-27)።

**12:6**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"የምድር እቶን"** |
| **አኪጀት** | **"የምድር እቶን"** |
| **አየተመት** | **"የመሬት እቶን"** |
| **አኢመቅ** | **"ከምድር የሚወጣ"** |
| **ጄፒኤስኦኤ** | **"ምድራዊ እቶን"** |
| **የተእመቅ** | **"በመሬት የተፈተነ"** |

"እቶን" ተብሎ የተተረጎመው ቃል በብኪ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው (ቢዲቢ 760፣ ኬቢ 833)። ብዙ ሊቃውንት የሚያምኑት ሙያዊ ቃላት እንደሆነ ነው፣ ከብረታ ብረት ጋር የተያያዘ፣ ምድራዊ ምድጃ ከአፈር ወይም ከሸክላ መሬት ላይ የተሠራ።

"ኤምቲ" "ምድር ላይ" የሚል አለው፣ ወይም "በመሬት ላይ፣" እሱም ከአፈር የተበጀውን ቅርጽ ማውጫ የሚያመለክት፣ የቀለጨው ብር የሚፈስስበት።

▣ **"ሰባት ጊዜ"** ሰባት ተምሳሌታዊ የፍጽምና ቁጥር ሲሆን፣ የተገኘውም ከሰባቱ የፍጥረት ቀናት ነው፣ የዘፍጥረት 1-2።

## ልዩ ርዕስ፡ ተምሳሌት (ምልክት) ቁጥሮች በቅዱስ ቃሉ

*ሀ. አንዳንድ ቁጥሮች እንደ መቁጠሪያ እና ተምሳሌት ያገለግላሉ፡*

1. አንድ — እግዚአብሔር (ምሳሌ፣ ዘዳ. 6፡4፤ ኤፌ. 4፡4-6)
2. ስድስት — የሰው የፍጽምና ጉድለት (ከ7 አንድ ሲቀነስ፣ ምሳሌ፣ ራዕ. 13፡18)
3. ሰባት — መለኮታዊ ፍጽምና (ሰባቱ የፍጥረት ቀናት)። በራዕይ ያሉትን ተምሳሌታዊ አጠቃቀሞች ተገንዘብ።
   ሀ. ሰባት መቅረዞች፣ 1፡12፣20፤ 2፡1
   ለ. ሰባት ኮከቦች፣ 1፡16፣20፤ 2፡1
   ሐ. ሰባት ቤተ-ክርስቲያናት፣ 1፡20
   መ. ሰባቱ የእግዚአብሔር መናፍስት፣ 3፡1፤ 4፡5፤ 5፡6
   ሠ. ሰባት መብራቶች፣ 4፡5
   ረ. ሰባት ማኅተሞች፣ 5፡1፣5
   ሰ. ሰባት ቀንዶች እና ሰባት ዓይኖች፣ 5፡6
   ሸ. ሰባት መላእክት፣ 8፡2፣6፤ 15፡1፣6፣7፣8፤ 16፡1፤ 17፡1
   ቀ. ሰባት መለከቶች፣ 8፡2፣6
   በ. ሰባት ነጎድጓድ፣ 10፡3፣4
   ተ. ሰባት ሺህ፣ 11፡13
   ቸ. ሰባት ራሶች፣ 13፡1፤ 17፡3፣7፣9
   ኀ. ሰባት መቅሠፍቶች፣ 15፡1፣6፣8፤ 21፡9
   ነ. ሰባት ጎድጓዳ ሳህኖች፣ 15፡7
   ኘ. ሰባት ነገሥታት፣ 17፡10
   አ. ሰባት ጽዋዎች፣ 21፡9
4. አስር — ፍጽምና
   ሀ. በወንጌል አጠቃቀማቸው፡
      (1) ማቴ. 20፡24፤ 25፡1፣28
      (2) ማርቆስ 10፡41
      (3) ሉቃስ 14፡31፤ 15፡8፤ 17፡12፣17፤ 19፡13፣16፣17፣24፣25
   ለ. በራዕይ አጠቃቀሙ፡
      (1) 2፡10፣ የአስሩ ቀን መከራ
      (2) 12፡3፤ 17፡3፣7፣12፣16፣ አስር ቀንዶች
      (3) 13፡1፣ አስር ዘውዶች
   ሐ. የ10 ብዜት በራዕይ፡
      (1) 144,000=12×12×1,000፣ ዝከ. 7፡4፤ 14፡1፣3
      (2) 1,000= 10×10×10፣ ዝከ. 20፡2፣3፣6
5. አስራ ሁለት — የሰው አደረጃጀቶች
   ሀ. የያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች (ማለትም፣ የእስራኤል አስራ ሁለት ነገዶች፣ ዘፍ. 35፡22፤ 49፡28)
   ለ. አስራ ሁለት ዐምዶች፣ ዘጸ. 24፡4
   ሐ. አስራ ሁለት የዕንቁ ድንጋዮች፣ በሊቀ ካህኑ ደረት ላይ የሚሆኑ፣ ዘጸ. 28፡21፤ 39፡14
   መ. አስራ ሁለት ሙልሙል ዳቦዎች፣ በቅዱስ ስፍራ ጠረጴዛ ላይ የሚሆኑ (ለእግዚአብሔር የአስራ ሁለቱ ነገዶች በጋቢነት ተምሳሌት)፣ ሌዋ. 24፡5፤ ዘጸ. 25፡30
   ሠ. አስራ ሁለት ሰላዮች፣ ዘዳ. 1፡23፤ ኢያ. 3፡22፤ 4፡2፣3፣4፣8፣9፣20
   ረ. አስራ ሁለት ሐዋርያት፣ ማቴ. 10፡1
   ሰ. በራዕይ አጠቃቀሙ፡
      (1) አስራ ሁለት ሺህ የታተሙ፣ 7፡5-8
      (2) አስራ ሁለት ከዋክብት፣ 12፡1
      (3) አስራ ሁለት ደጆች፣ አስራ ሁለት መላእክት፣ አስራ ሁለት ነገዶች፣ 21፡12
      (4) አስራ ሁለት የመሠረት ድንጋዮች፣ የአስራ ሁለቱ ሐዋርያት ስሞች፣ 21፡14
      (5) አዲሲቱ ኢየሩሳሌም አስራ ሁለት ሺህ ስኴር ሜዳ ነች፣ 21፡16
      (6) አስራ ሁለት ደጆች ከአስራ ሁለት እንቁ የተሠሩ፣ 21፡12
      (7) የሕይወት ዛፍ አስራ ሁለት ዓይነት ፍሬዎች፣ 22፡2
6. አርባ —የጊዜ ቁጥር፡
   ሀ. አንዳንዴ በጥሬው (ዘጸዓት እና የምድረ በዳ መንከራተት፣ ምሳ. ዘጸ. 16፡35)፤ ዘዳ. 2፡7፤ 8፡2
   ለ. በጥሬው ወይም ተምሳሌታዊ ሊሆን ይችላል
      (1) የጥፋት ውኃ፣ ዘፍ. 7፡4፣17፤ 8፡6

(2) ሙሴ በሲና ተራራ፣ ዘጸ. 24፡18፤ 34፡28፤ ዘዳ. 9፡9፣11፣18፣25
(3) የሙሴ ሕይወት ምድቦች፡
(ሀ) አርባ ዓመት በግብፅ
(ለ) አርባ ዓመት በምድረ በዳ
(ሐ) አርባ ዓመት እስራኤልን በመምራት
(4) ኢየሱስ አርባ ቀናት ጾመ፣ ማቴ. 4፡2፤ ማርቆስ 1፡13፤ ሉቃስ 4፡2
ሐ. (በኀብራዊ መልኩ) ይህ ቁጥር የሚከሰትበት ጊዜ ብዛት ከጊዜ አኳያ መጽሐፍ ቅዱስ መመደቡን (መለየቱን) ተገንዘብ!
7. ሰባ — ለሕዝብ የጥቅል ቁጥር፡
ሀ. እስራኤል፣ ዘጸ. 1፡5
ለ. ሰባ ሽማግሌዎች፣ ዘጸ. 24፡1፣9
ሐ. የፍጻሜ መዳረሻ፣ ዳን. 9፡2፣24
መ. የተልዕኮ ቡድን፣ ሉቃስ 10፡1፣17
ሠ. ይቅርታ (70×7)፣ ማቴ. 18፡22
ለ. የተሻሉ ማጣቀሻዎች
1. ጆን ጄ. ዳቪስ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ሥነ-ቁጥር
2. ዲ. ብሬንት ሳንዲ፣ ማረሻና መኮትኮቻ መንጠቆ

**12፡7 “ጠብቀን… ታደገን”** እነዚህ ግሦች (ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ እና ቢዲቢ 665፣ ኬቢ 718፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ) በርካታ ጊዜ መዝሙር ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል፣ የዘማሪውን ጩኸት ወደ ያህዌ መገኛ ለመግለጽ፣ በተቃዋሚዎች ወይም ሁኔታዎች ላይ እንዲነሣ።

▣ **“ከዚህ ትውልድ”** ይህ መዝሙር 12 ላይ የሚገኘው ሐረግ የሚያመለክተው
1. ሐሰትን የሚናገሩትን፣ ቁ. 2
2. የሽንገላ አንደበት ያላቸውን፣ ቁ. 2
3. መንታ ልብ ያላቸውን፣ ቁ. 2
4. ስለራሳቸው ታላቅ ነገር የሚናገሩትን፣ ቁ. 3-4
5. ችግረኛን የሚያጠፉትን፣ ቁ. 5
6. ክፉዎች የሚኮሩ፣ ቁ. 8

▣ **“ለዘላለም”** ይህ የያህዌ መጠሪያ ሊሆን ይችላል፣ “ዘላለማዊው” (AB ገጽ 75)። እንደዚያ ከሆነ እሱ ያህዌን ትይዩ ያደርጋል፣ ቀደም ባለው ስንኝ ቅኔ ላይ።

**12፡8**

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመት** | **“ምናምንቴ”** |
| **አኢመቅ** | **“ከንቱነት”** |
| **ጄፒኤስኦኤ** | **“ወራዳነት”** |
| **የተእመቅ** | **“የማይረባ”** |

ይህ ስም (ቢዲቢ 273) በብኪ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው። የግሡ ዓይነት ፍችው (ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 1109)
1. በ*ቃል* “ቸልተኛ መሆን” ወይም “የተዋረደ መሆን”
2. በ*ሂፊል*፣ “ለቀቅ አድርጎ መያዝ”

አንዱ መመልከት ሊሞክር ይችላል፣ ሁለቱ የቁ. 8 ስንኞች ትይዩ ተመሳሳይን ሊፈጥሩ እንደቻሉ፣ ሌሎች ጽሑፋዊ እርማት ሐሳብ የተሰጠባቸውን።
1. ዳግም የድምጽ ቃና የተሰጣቸውን — “የሞራል ተወቃሽ”
2. የተለየ ታሳቢ ሥርወ-ቃል — “አዘቅት”
3. ዕርማት — “የተሰረቁ ዕቃዎች” (ዝክ. LXX)
4. ዕርማት — “ኮከባዊ አካላት”

በዚህ ሥነ-መለኮታዊ ጉዳይ የተሻለ የሚመስለው፣ የአልፎ-አልፎ ቃላት መካተት
1. የሙሉውን መዝሙር ፍች
2. የአንጓውን ማዕከላዊ እውነት
3. የስንኞቹን ታሳቢ ትይዩነት
4. ታሳቢ ተዛማጅ ሥርወቃላት

የተሻለውን ግምት ይሰጡናል!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወስን አይደለም።

1. ልበ-መንታ ምንድነው (ቁ. 2) ?
2. ቁጥር 4 ምን ማለት ነው?
3. ሰዋዊ ቃላት እጅግ ጠቃሚ የሚሆኑት ለምንድነው?

## መዝሙር 13
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| በችግር ጊዜ የርዳታ ጸሎት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>"ለመዘምራን አለቃ የዳዊት መዝሙር" | በጌታ ማዳን መታመን | ከግል ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት (ሰቆቃ) | የርዳታ ጸሎት | የእምነት ጥሪ |
| 13:1-2 | 13:1-2 | 13:1-2 | 13:1-2 | 13:1-3 |
| 13:3-4 | 13:3-4 | 13:3-4 | 13:3-4 | |
| | | | | 13:4-5 (6) |
| 13:5-6 | 13:5-6 | 13:5-6 | 13:5-6 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 13፡1-2**

**1 አቤቱ፥ እስከ መቼ ፈጽመህ ትረሳኛለህ?**
**እስከ መቼስ ፊትህን ከእኔ ትሰውራለህ?**
**2 እስከ መቼ በነፍሴ እመካከራለሁ?**
**ትካዜስ እስከ መቼ ሁልጊዜ ይሆናል?**
**እስከ መቼ ጠላቴ በላዬ ይጓደዳል?**

**13፡1-2** የዚህ መግቢያ አንጓ አወቃቀር "እስከ መቼ" እንደሆነ ተገንዘብ (ቢዲቢ 723 II፣ መዝ. 6:3፤ 90:13) ጥያቄዎች።
1. ቁጥር 1 ላይ ሁለት
2. ቁጥር 2 ላይ ሁለት

እነርሱ ጽሑፋዊ መንገዶች ናቸው፣ የመዝሙረኛውን ተስፋ መቁረጥ የሚገልጹ፣ አሁን ባለበት ሁኔታ። በእግዚአብሔር እንደተተወ ተሰምቶታል።
1. በእግዚአብሔር መረሳት፣ ቁ. 1ሀ
2. እግዚአብሔር ራሱን ደብቋል፣ ቁ. 1ለ
3. ግለሰባዊ ኀዘን፣ ቁ. 2ሀ፣ለ
4. ጠላቱ ከፍ ከፍ ብሏል፣ ቁ. 2ሐ

ቁ. 1 እና ቁ. 2 ደግሞ አንድ ላይ መዝ. 10፡11 ላይ እንደሚከሰቱ ተገንዘብ። የመተው ትዕይንታዊ ጭብጥ መዝሙር 42 ላይ መልካም ሆኖ ተገልጿል። የመተው ስሜት የተጎዳው መዝሙረኛ አስተሳሰብ ብቻ ነው። እውነታው ያህዌ ከእኛ ጋር፣ ለእኛ፣ እና በእኛ በኩል በተገቢው ጊዜና ሰዓት መሥራቱ ነው!

**13፡1 "ዘላለም"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 664) ግነታዊ ፈሊጥ ነው የመዝሙረኛውን ስሜት የሚገልጽ፣ በእግዚአብሔር በቋሚነት እንደተተወ።

◘ ***"ፊት"*** ይህም ደግሞ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ለአካላዊ መገኘት (መዝ. 11:7፤ 17:15፤ 27:4፣8)። በሆነ ምክንያት (ማለትም፣ የግል ኃጢአት፣ መዝ. 13፡3ለ ወይም ሕመም፣ 3ለ) ያህዌ ዞር የሚል ይመስላል።

**13፡2 "ነፍስ... ልብ"** እነዚህ ሁለቱ ትይዩ ናቸው፣ እናም የዕብራውያንን ግለሰባዊ ሰውኛ መግለጫዎች።

◘ **"ሁልጊዜ"** ይህ ፈሊጥ ፍችው "ዘወትር" ነው። ይህ ማለት ኀዘኑ በቀን ብርሃን ጊዜያት ያበቃል ማለት አይደለም።

> ***መዝሙር ፡ 13፡3-4***
> **[3]አቤቱ አምላኬ፥ እየኝ ስማኝም፣**
> **ጠላቴ አሸነፍሁት እንዳይል፥**
> **[4]የሚያስጨንቁኝም እኔ ብናወጥ ደስ እንዳይላቸው፥**
> **ለሞትም እንዳልተኛ ዓይኖቼን አብራ።**

**13፡3-4** ይህ አንጓ ለእግዚአብሔር የሚደረግ ጸሎት ነው፣ ለጸሎት ጥያቄው ምላሽ እንዲሰጠው ቁ. 1-2።
ተለጣጣቂ ሦስት ተተኳሪዎች አሉ (ማለትም፣ የጸሎት ጥያቄዎች)።

1. መገንዘብ ("መመልከት") — ቢዲቢ 613፣ ኬቢ 661፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 80:14፤ ሰቆ. 1:11፤ 2:20፤ 5:1
2. መልስ – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. መብራት ("እንዲያበራ ማድረግ") – ቢዲቢ 21፣ ኬቢ 24፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፤ ይህ ጥቅም ላይ የዋለበት ስሜት
   ሀ. እግዚአብሔር ጸሎቴን መለሰ፣ በእናንተ ፊት (መዝ. 6:7፤ 19:8)
4. ለ. እግዚአብሔር ከሞት አዳነኝ (መዝ. 38:10)

ደግሞም አአመመቅ "በፍራቻ" ሦስት ጊዜ (ኤምቲ፣ ቢዲቢ 814፣ ሁለቱ እንዳለው ተገንዘብ)።

1. እንዳልሞት
2. ጠላቴ እንዳይጮኽ
3. ጠላቶቼ ደስ እንዳይሰኙ

> ***መዝሙር ፡ 13፡5-6***
> **[5]እኔ ግን በቸርነትህ *ታመንሁ*፥**
> **ልቤም በመድኃኒትህ ደስ ይለዋል።**
> **[6]የረዳኝን እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ፥**
> **ለልዑል እግዚአብሔር ስምም እዘምራለሁ።**

**13፡5-6** ይህ የመዝሙረኛው የእምነት/መታመን/ሃይማኖት መግለጫ ነው፣ በያህዌ።

1. ታምኛለሁ (ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል የተጠናቀቀ*) በደግነትህ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5:7 ላይ) መታመን ዋነኛ ገጽታ ነው፣ የእውነተኛ አማኝ (መዝ. 25:5፤ 42:5፤ 65:5፤ 78:22፤ 86:2)። ሙሉ ማስታወሻ መዝ. 4:5 ላይ ተመልከት።
2. ደስ ይለኛል (ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189፣ *ቃል ተጽዕኖዊ*) በማዳንህ (ልዩ ርዕስ መዝ. 3:7 ላይ ተመልከት)፣ እሱም በዐውደ-ጽሑፉ የጤና መመለስን የሚጠቅስ።
3. እዘምራለሁ (ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ *ቃል ተጓዳኝ*)።

በዕብራይስጥ አስተሳሰብ ሞት ወደ ሲኦል መውረጃ ነው፣ እዚያ ማንም እግዚአብሔርን የማያመሰግንበት(መዝ. 6:5፤ 30:9፤ 88:10-12፤ 115:17፤ ኢሳ. 38:18)። ልዩ ርዕስ ተመልከት: ሙታን የት ናቸው? መዝ. 1:6 ላይ። 6:5 እና 9:13 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

መዝሙረኛው እምነቱን የመሠረተው በያህዌ ባሕርይና ድርጊት ላይ ነው (ማለትም፣ "ከእኔ ጋር በሙላት ያደርጋል፣" ቢዲቢ 168፣ ኬቢ 197፣ *ቃል የተጠናቀቀ*)።

**13፡6 “ለእኔ በቸርነት አድርጓል”** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 168፣ ኬቢ 197፣ *ቃል የተጠናቀቀ*) በርካታ ጊዜ መዝሙር ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ (መዝ. 116:7፤ 119:17፤ 142:7)። ይህ የተጠናቀቀ ዓይነት፣ የመዝሙረኛውን ርግጠኝነት ያመለክታል፣ ያህዌ በእርሱ በኩል ወደፊት እንደሚሠራ፣ እና ስለዚህ፣ እሱን ልክ ቀደም ብሎ እንደተደረገ ያስቀምጠዋል።

▣ **“ከእኔ ጋር”** ባስገራሚ መልኩ LXX ይህንን የእግዚአብሔር መጠሪያ የሚተረጉመው — “ልዑሉ” በሚል ነው (አኢመቅ)። ይኸው ተመሳሳይ ለውጥ ደግሞ መዝ. 7፡8 ላይ ይከሰታል።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ቁጥር 1-2 ታማኝ ተከታዮች በወደቀው ዓለም ላይ ምን እንደሚሰማቸው ይገልጻል። ይህንን በራስህ ቋንቋ ግለጽ።
2. ሞት “እንቅልፍ” ነውን?
3. “ቸርነትን” ግለጽ አብራራም።
4. “ደኅንነት” የሚለው ቃል ትርጉሙን ከብኪ ወደ አኪ እንዴት ይለውጣል?

## መዝሙር 14
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጆት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የሰዎች ሞኝነትና ኃጢአተኝነት <u>ኤምቲ መግቢያ</u> “ለመዘምራን አለቃ የዳዊት መዝሙር” | የአምላክ-የለሾች ሞኝነትና የአምላክ የመጨረሻ ድል | የከፋተኛና የኃጢአተኛ ዓለም ኩነኔ (መዝ. 53) | የሰው ክፋት (መዝሙር 53 | የአምላክ -የለሽ ዕጣ |
| 14:1-3 | | | 14:1 | |
| | 14:1 | 14:1 | | 14:1 |
| | | | 14:2-3 | |
| | 14:2-3 | 14:2 | | 14:2 |
| | | 14:3 | | 14:3 |
| 14:4-6 | | | 14:4 | |
| | 14:4-6 | 14:4-6 | | 14:4 |
| | | | 14:5-6 | |
| | | | | 14:5-6 |
| 14:7 | | | 14:7 | |
| | 14:7 | 14:7 | | 14:7 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 14፡1-3**

**[1]ሰነፍ በልቡ። አምላክ የለም ይላል።**
**በሥራቸው ረከሱ፥**
**ጐስቈሉ በጎ ነገርን የሚሠራ የለም።**
**[2]የሚያስተውል እግዚአብሔርንም የሚፈልግ እንዳለ ያይ ዘንድ**
**እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ።**
**[3]ሁሉ ዐመፁ በአንድነትም ረከሱ**
**በጎ ነገርን የሚሠራ የለም አንድም ስንኳ የለም።**

**14፡1 “ሰነፍ”** ይህ መዝሙር በትክክል መዝሙር 53ን ይመስላል። ይህ ቃል (ቢዲቢ 614 I) የሚያመለክተው ያህዌን የሚያውቁ ሰዎች ሆነው ነገር ግን እሱ ሕይወታቸው ላይ ተጽዕኖ እንደሌለው በመምረጥ የሚኖሩ ናቸው። ምንም አምላክ-የለሽ በፍልስፍናዊ መልኩ በ*ጥቅም* (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አልነበረም፣ ነገር ግን አብዛኞቹ የኪዳኑ ሕዝቦች በተግባር አምላክ-የለሾች ነበሩ (ዘዳ. 32:6፣21፤ 2 ሳሙ. 13:13፤ መዝ. 10:4፣11፣13፤ 53:1፤ 74:22፤ ሕዝ. 13:3)። የሉቃስ 12:48 ምሳሌ የሚያመለክተው እንደዚያ ዓይነቶቹን ሰዎች ነው።

▣ “ሰነፍ” እንዴት አድርጎ እንደተሳለ ተገንዘብ።
1. ተበላሽተዋል – ቢዲቢ 1007፣ ኬቢ 1469፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ (ማለትም፣ የተመቻቸ ሁኔታ)

2. ርኵስ ነገርን ይሠራሉ – ቢዲቢ 1073፣ ኬቢ 1765፣ ሂፊል የተጠናቀቀ (ማለትም፣ የተመቻቸ ሁኔታ)

◘ **"ርኵስ ድርጊት"** ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ ርኵሰት (ጸያፍ) (ብኪ)

"ርኵሰቶች" (ቢዲቢ 1072) በርካታ ነገሮችን ሊያመለክት ይችላል፡

1. ከግብፃውያን ጋር የተያያዙ ነገሮች፡
   ሀ. እነርሱ ከዕብራውያን ጋር መመገብን እንደ ርኵሰት ይቆጥሩ ነበር፣ ዘፍ. 43፡32
   ለ. እነርሱ ከብት አርቢዎችን ይጸየፉ ነበር፣ ዘፍ. 46፡34
   ሐ. እነርሱ የዕብራውያንን መሥዋዕት ይጸየፉ ነበር፣ ዘጸ. 8፡26
2. ያህዌ ከእስራኤል ድርጊቶች ጋር ካለው ስሜት ጋር የተያያዙ ነገሮች፡
   ሀ. ርኵስ ምግብ፣ ዘዳ. 14:2
   ለ. ጣዖታት, ዘዳ. 7:25፤ 18:9,12፤ 27:15
   ሐ. የጣዖት መናፍስተኞች, ዘዳ. 18:9,12
   መ. ሕፃናትን ለሞሎክ ማቃጠል, ሌዋ. 18:21-22፤ 20:2-5፤ ዘዳ. 12:31፤ 18:9,12፤ 2 ነገ. 16:3፤ 17:17-18፤ 21:6፤ ኤር. 32:35
   ሠ. የከነአናውያን ጣዖት አምልኮ, ዘዳ. 13:14፤ 17:4፤ 20:17-18፤ 32:16፤ ኢሳ. 44:19፤ ኤር. 16:18፤ ሕዝ. 5:11፤ 6:9፤ 11:18,21፤ 14:6፤ 16:50፤ 18:12
   ረ. ነውር ያለባቸውን እንስሳት መሠዋት, ዘዳ. 17:1 (ዝከ. 15:19-23፤ ሚል. 1:12-13)
   ሰ. ለጣዖት መሠዋት, ኤር. 44:4-5
   ሸ. ቀደም ብሎ የፈቷትን ሴት መልሶ ማግባት፣ ዘዳ. 24:2
   ቀ. የወንድ ልብስ የሚለብሱ ሴቶች (የከነአናውያን አምልኮ ሊሆን ይችላል), ዘዳ. 22:5
   በ. የባዕድ አምልኮ ግልሙትና የተገኘ ገንዘብ (የከነአናውያን አምልኮ), ዘዳ. 23:18
   ተ. የእስራኤል ባዕድ አምልኮ, ኤር. 2:7
   ቸ. ግብረ-ሰዶማውያንነት (የከነአናውያን ባዕድ አምልኮ ሊሆን ይችላል), ሌዋ. 18:22፤ 20:13
   ኀ. ሐሰተኛ ሚዛንን መጠቀም፣ ዘዳ. 25:16፤ ምሳ. 11:1፤ 20:23
   ነ. የተጣሱ የምግብ ሕግጋት (የከነአናውያን አምልኮ ሊሆን ይችላል), ዘዳ. 14:3
3. የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ ምሳሌዎች:
   ሀ. ምሳሌ 3:32፤ 6:16-19፤ 11:1,20፤ 12:22፤ 15:8,9,26፤ 16:5፤ 17:15፤ 20:10,23፤ 21:27፤ 28:9
   ለ. መዝሙር 88:8
   ሐ. ኢዮብ 30፡10
4. ተደጋጋሚ የፍጻሜ ዘመን ሐረግ አለ "የጥፋት ርኵሰት" እሱም ዳንኤል ላይ ጥቅም ላይ የዋለ (ዝከ. 9:27፤ 11:31፤ 12:11)። እሱም ሦስት የተለያዩ ሁነቶችን የሚያመለክት ነው (ባለ ብዙ ፍጻሜ ትንቢት)፡
   ሀ. አንቲከስ IV ኢፒፋነስ የበይነ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ መቃብያን ጊዜ (1 መቃ. 1፡54፣59፤ 2 መቃ. 6፡1-2)
   ለ. የሮማ ጀነራል(ኋላ ላይ ንጉሥ የሆነ)፣ ቲቶ፣ እሱም ኢየሩሳሌምን ያጠፋና መቅደሱን የደመሰሰ፣ በ70 ዓ.ም (ማቴ. 24:15፤ማርቆስ 13:14፤ ሉቃስ 21:20)
   ሐ. የፍጻሜ ዘመን የዓለም መሪ፣ "የዓመጽ ልጅ" ተብሎ የሚጠራ" (2 ተሰ. 2:3-4) ወይም "የክርስቶስ ተቃዋሚ" (1 ዮሐንስ 2:18፤ 4:3፤ ራዕይ 13)

◘ ***"በጎ ነገርን የሚሠራ የለም አንድም ስንኳ የለም።"*** ይህ አጠቃላይ መግለጫ ነው፣ የወደቀው ሰው-ልጅ መንፈሳዊ ሁኔታ፣ የኪዳኑ ሕዝቦች እንኳ ቢሆኑ። እሱም መዝ. 14፡2-3 ላይ ተብራርቷል። የወደቀው ሰው ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳለው ተገንዘብ።

1. በጎ ነገርን የሚያደርግ የለም፣ ቁ. 1፣3 (አካታች)
2. የሚያስተውል የለም
3. እግዚአብሔርን የሚፈልግ የለም
4. ሁሉም ገለል ብለዋል (ቁ. 3 ላይ ማስታወሻ ተመልከት)
5. ሁሉም ተበላሽተዋል

አንዱ ዘፍጥረት 3 በሰው ልጆች ሁሉ ላይ ያሳደረውን ተጽዕኖ ሊመለከት ይችላል። ጳውሎስ ጠንካራና ተለጣጣቂ ቁጥሮችን አንድ ላይ አስቀምጧል፣ በሰው ልጅ ዓመጸኝነት ላይ፣ ሮሜ 3:9-18፣23። እሱም መዝ. 14:1-3፤ 53:1-4፤ 5:9፤ 140:3፤ 10:7፤ ኢሳ. 59:7-8፤ መዝ. 36:1ን ጠቅሷል። ይህ እውነት የመጀመሪያው የወንጌል እውነት ነው (ሮሜ. 1:18-3:18)። ወንጌል "የምስራች" ነው፣ በክፉ ዜና ላይ!

**14፡2 "እግዚአብሔር ከሰማይ ተመለከተ"** ያህዌ ያህዌ በሰማይ በመኖሩ ይመለከታል (ልዩ ርዕስ መዝ. 8፡1 ላይ ተመልከት)፣ እሱም እዚያ ሆኖ በምድር ላይ የሚሆነውን ሁሉ ይመለከታል፣ ያውቃልም (ድርጊትን፣ ሐሳብን፣ ፍላጎትን፣ መዝ. 33:13፣14፤ 102:19፤ ኢዮብ 28:24)። ያህዌ፣ ከጣዖታት እጅግ በተለየ መልኩ ይመለከታል፣ ያውቃል፣ ያደርጋልም!

**14:3 "ሁሉም ወደ ጎን ዞር አሉ"** የያህዌ ኪዳን ጥርት ብሎ የተመለከተ መንገድ/ፋና/ጎዳና ነው። የእርሱ ሕዝቦችም በዚህ ቀጥተኛ (ማለትም፣ የጽድቅ) እና ጠባብ መንገድ እንዲሆኑ ነበር፣ እነርሱ ግን አላደረጉም። (ዘጸ. 32:8፤ ዘዳ. 9:12፤ 11:16፤ 17:11፣17፤ መሳ. 2:17፤ 1 ሳሙ. 12:20፤ 2 ነገ. 22:2፤ ኤር. 5:23፤ 17:13፤ 32:40)። ዞር ማለታቸው ከአለማወቅ አይደለም ነገር ግን ሆን ተብሎ የተደረገ ዓመጻ ነው እንጂ!

**መዝሙር ፡ 14:4-6**

> **[4]ሕዝቤን እንደ እንጀራ የሚበሉ**
> **ኃጢአት የሚሠሩ ሁሉ በውኑ አያውቁምን?**
> **እግዚአብሔርንም አይጠሩትም።**
> **[5]በዚያ በታላቅ ፍርሃት እጅግ ፈሩ፥**
> **እግዚአብሔር በጻድቃን ትውልድ ዘንድ ነውና።**
> **[6]የድሆችን ምክር አሳፈራችሁ፥**
> **እግዚአብሔር ግን ተስፋቸው ነው።**

**14:4-6** ይህ አንጻ የሚያሳየው "ያለማወቅን" ውጤት ነው (ቢ.ዲ.ቢ 393፣ ኬቢ 390፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡ 6 ላይ)። ክፉው በድሀ፣ በችግረኛ እና ምንም ድምፅና አቅም በሌላቸው ላይ የሚያደርገው፣ በእግዚአብሔር ፍርድ ያገኛል፣ በጠባቂያቸው (ዘዳ. 10:17-19፤ 14:29፤ 24:17፣19-22፤ 26:12፣13፤ 27:19)!

እሱ "መታመኛቸው" ነው (ቢ.ዲ.ቢ 340፣ መዝ. 2:12፤ 5:11፤ 34:22)። እነሱን ማጥቃት እሱን ማጥቃት ነው። እሱ ይከላከልላቸዋል።

**14:4**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት፣** | |
| **አየተመት፣ LXX** | **"እግዚአብሔርን አይጠሩትም"** |
| **አእቅ** | **"ለእኔም ፈጽሞ አይጸልዩም"** |
| **አኢመቅ፣ የተእመቅ** | **"ያህዌን ፈጽሞ አይጠሩትም"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"እግዚአብሔርን አይለምኑትም"** |

ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ 894፣ ኬቢ 1128፣ የተጠናቀቀ) የተለመደው ዓይነት ነው፣ በብዙ መንገዶች ጥቅም ላይ የሚውል (ማለትም፣ ሰፊ የፍች መስክ)። በመዝሙራት እሱ በርካታ አጠቃቀሞች አሉት።

1. ለካህናት በአምልኮና በጸሎት — መዝ. 99:6
2. ለኪዳኑ ሕዝቦች ጸሎት – መዝ. 4:2፤ 20:10፤ 50:15፤ 86:5፤ 91:15፤ 107:6፣13፤ 116:2፤ 141:1
3. አሕዛብ ያህዌን አይጠሩትም (ማለትም፣ መዝ. 79:6) እስራኤል ግን ይጠሩታል – መዝ. 14:4፤ 50:15፤ 53:4

በአኪ፣ ይህ የብኪ የአምልኮ ሐረግ (ማለትም፣ የአምልኮ ሥርዓትና ጸሎት) በኢየሱስ ወደ ያህዌ ግንኙነት መግቢያ፣ መቅረቢያ መግለጫ መንገድ ሆኗል (ሐዋ. 2:21፤ 22:16፤ ሮሜ. 10:9-13)።

እኛ የተጠራን ሰዎች ነን፣ የጌታን ስም የምንጠራ፣ ከዚያም ለአገልግሎት የተጠራን! ጸሎት-የለሽነት የስሕተት እምነት ምልክት ነው፣ እናም ተግባራዊ አምላክ-የለሽነት!

**14:5 "በዚያ በታላቅ ፍርሃት እጅግ ፈሩ፥"** ይህ በጥሬው "ፍርሃትን ፈሩ" ነው (የተጠናቀቀ እና የተመሳሳይ ሥር ስም — ቢ.ዲ.ቢ 808፣ ኬቢ 922)።

"በዚያ" ያልተገለጸ እስከሆነ ድረስ፣ አንዳንዶች የሚያስቀምጡት ከሐረጉ መጨረሻ ላይ ነው፣ እናም "ፍርሃት በሌለበት" የሚል ያክሉበታል (ኤቢ፣ አኢመቅ)።

**መዝሙር ፡ 14:7**

> **7ከጽዮን መድኃኒትን ለእስራኤል ማን ይሰጣል?**
> **እግዚአብሔር የሕዝቡን ምርኮ በመለሰ ጊዜ፥**
> **ያዕቆብ ደስ ይለዋል፥ እስራኤልም ሐሤት ያደርጋል።**

**14:7 "አቤቱ የእስራኤል መድኃኒት"** ይህ የያህዌ መጠሪያ ነው፣ በጽዮን የሚኖረው (ማለትም፣ የሞሪያ ተራራ፣ መቅደስ)። "የያህዌን" ትይዩ ስንኝ (መስመር) 2 ላይ ተመልከት።

ይህ ቁጥር ደግሞ መዝ. 53:6 ላይ ይገኛል፣ ማለትም እሱ ምሳሌያዊ ሊሆን ይችላል። LXX ይህን የመጀመሪያ ስንኝ ጥያቄ ያደርገዋል (ዝክ. 53:6)።

▣ **"ይሰጣል"** ይኸው ተመሳሳይ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ 996፣ ኬቢ 1427) ደግሞ ሊሆን የሚችለው "መጸጸት" ወይም "ወደ ኋላ መመለስ" ነው። ሆኖም፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ እስራኤል ለንስሐ አልተጠራም።

የቃላት ጨዋታ አለ፣ "በመመለስ" (ቢዲቢ 996) እና "በመታደል" መካከል (ቢዲቢ 986) አኢት መጽሐፍ ቅዱስ "በመዞር ዞሯል (ወደ) ሕዝቡ" የሚል አለው።

◘ **"ያዕቆብ... እስራኤል"** አባት ያዕቆብ አስራ ሁለት ልጆች ነበሩት፣ እነርሱም አስራ ሁለት ነገዶች የሆኑ። የያዕቆብ ስም ወደ እስራኤል ተቀይሯል፣ ዘፍ. 32፡22-32 ላይ።

**ልዩ ርዕስ፡ እስራኤል (ስሙ)**

I. የስሙ ፍቺ ርግጠኝነት የለውም (ቢዲቢ 975)።
   ሀ. ኤል የዘላለም
   ለ. ኤል የዘላለም (ተጽዕኗዊ)
   ሐ. ኤል ጠባቂው
   መ. ኤል ይታገላል
   ሠ. ኤል እጅግ ይጥራል
   ረ. እሱም ከእግዚአብሔር ጋር ታግሏል (ዘፍ. 32፡28)
II. በብሉይ ኪዳን አጠቃቀሙ
   ሀ. የያዕቆብ ስም (ነጣቂ፣ ተረከዝ ያዥ፣ ቢዲቢ 784፣ ዝከ. ዘፍ. 25፡26) በያቦቅ ወንዝ ላይ ከመንፈሳዊ አካሉ ጋር ከታገለ በኋላ ተቀየረ (ዘፍ. 32:22-32፤ ዘጸ. 32:13)። የዕብራይስጥ ስሞች ፍቺ ዘወትር ድምፅን ተከትሎ የሚሄድ ነው፣ ሥርወ ቃልን ሳይሆን (ዝከ. 32፡28)። ስሙም እስራኤል ሆኗል (ምሳሌ፣ ዘፍ. 35፡10)።
   ለ. እሱም ለአስራ ሁለት ልጆቹ የጥቅል ስም ሆኖ ያገለግላል (ምሳሌ፣ ዘፍ. 32:32፤ 49:16፤ ዘጸ.1:7፤ 4:22፤ 28:11፤ ዘዳ. 3:18፤ 10:6)።
   ሐ. እሱም በአስራ ሁለቱ ነገዶች የሚመሠረተውን ሕዝብ የሚያመለክት ነው፣ ከዘጸዓት በፊት (ዘፍ. 47:27፤ ዘጸ. 4:22፤ 5:2) እና በኋላ (ዘዳ. 1:1፤ 18:6፤ 33:10)።
   መ. ከሳኦል፣ ዳዊት፣ እና ሰለሞን አህዳዊ ንጉሣዊ አገዛዝ በኋላ፣ ነገዶቹ ተከፍለዋል፣ በሮቦአም ሥር (1ኛ ነገሥ. 12)።
      1. ልዩነት የተጀመረው ይፋዊ መከፋፈል በፊት ነው (ምሳሌ፣ 2ኛ ሳሙ. 3:10፤ 5:5፤ 20:1፤ 24:9፤ 1 ነገሥ. 1:35፤ 4:20)
      2. የሰሜኑ ነገዶች የሚታወቁበት፣ ሰማርያ ወደ ሶርያ እስከ ወደቀ ድረስ፣ በ722 ዓ.ዓ (2ኛ ነገሥ. 17)።
   ሠ. ለይሁዳ በጥቂት ቦታዎች ጥቅም ላይ የዋለ (ምሳሌ፣ ኢሳይያስ 1፤ ሚክያስ 1:15-16)።
   ረ. ከሶርያና ከባቢሎን ስደት በኋላ እንደገና ለያዕቆብ ዝርዮች የጥቅል ስም ሆኗል (ምሳሌ፣ ኢሳ. 17:7፣9፤ ኤር. 2:4፤ 50:17፣19)።
   ሰ. ምዕመኑን ከካህናት በአንጻራዊነት ለመለየት (1ኛ ዜና 9:2፤ ዕዝራ 10:25፤ ነህ. 11:3)።

◘ **"ደስ ይለዋል... ሐሴትም ያደርጋል"** እነዚህ ሁለቱም ግሦች የመመለስን ውጤት ያለመክታሉ። ግሦች በዕብራይስጥ፣ የጊዜ ሁኔታቸውን የሚወስዱት ከዐውደ-ጽሑፉ ነው። ይህም ዐውደ-ጽሑፍ የወደፊት ነው።

1. ደስ ይለዋል — ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189፣ ተተኳሪ
2. ሐሴትም ያደርጋል – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ ያልተጠናቀቀ፣ በተተኳሪ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ሰነፍ ምን ማለቱ ነው፣ በእርሱ መግለጫ መሠረት፣ "እግዚአብሔር የለም"?
2. ብኪ ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኛ እንደሆኑ ያስተምራልን?
3. "እግዚአብሔርን መጥራት" ምን ማለት ነው?
4. ቁጥር 7 ስደትን ያመለክታልን?

## መዝሙር 15
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጽዮን ዜጋ መግለጫ<br>ኤምቲ መግቢያ “የዳዊት መዝሙር” | ከአምላክ ጋር የሚኖሩ ሰዎች ባሕርይ | ወደ መቅደስ ለመግባት የአምልኮ ሥርዓት | እግዚአብሔር ምን ይጠይቃል | የያህዌ እንግዳ |
| | | | 15:1 | |
| 15:1-5 | 15:1 | 15:1 | | 15:1 |
| | | | 15:2-5ለ | |
| | 15:2-5ለ | 15:2-5ለ | | 15:2-3ሀ |
| | | | | 15:3b-4ለ |
| | | | 15:5ሐ | |
| | 15:5ሐ | 15:5ሐ | | 15:4ሐ-5 |

## **የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

# የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 15፡1-5**

**1አቤቱ፥ በድንኳንህ ውስጥ ማን ያድራል?**
**በተቀደሰውም ተራራህ ማን ይኖራል?**
**2በቅንነት የሚሄድ፥ ጽድቅንም የሚያደርግ፥**
**በልቡም እውነትን የሚናገር።**
**3በአንደበቱ የማይሸነግል፥**
**በባልንጀራው ላይ ክፋትን የማያደርግ፥**
**ዘመዶቹንም የማይሰድብ።**
**4ኃጢአተኛ በፊቱ የተናቀ፥**
**እግዚአብሔርንም የሚፈሩትን የሚያከብር፥**
**ለባልንጀራው የሚምል የማይከዳም።**
**5ገንዘቡን በአራጣ የማያበድር፥**
**በንጹሑ ላይ መማለጃን የማይቀበል።**
**እንዲህ የሚያደርግ ለዘላለም አይታወክም።**

**15፡1 “ጌታ”** ይህ የኪዳን ስም ነው፣ ለመለኮት፣ ከዕብራይስጡ (የመሆን) ግሥ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፣ መዝ. 1፡1 ላይ።

◘ **"ማን"** ቁጥር 1 ጥያቄ ነው፣ ጽሑፋዊ ምልክት ሊሆን የሚችል፣ በበዓል ቀን ወደ መቅደሱ ለሚገቡት የአምልኮ ሥርዓት የሆነ።

◘ **"በድንኳንህ... በቅዱሱ ተራራህ"** እነዚህ ትይዩዎች ናቸው፣ ደግሞም ግሦቹን ("ማደር" እና "መኖር") የሚሉ። በያህዌ መቅደስ በቋሚነት የመሆን ጽንሰ-ሐሳብ (መዝ. 23፡6ለ) ከእግዚአብሔር ጋር ዘላለማዊ ኅብረት ማድረግ ነው፣ እርሱም

1. ከዚህ ሕይወት ባሻገር የሚደርስ
2. የቅርብ ኅብረትን የሚያካትት
3. የየቀኑ ገጽታ ያለው

መዝሙር 27፡4-6 ይህንኑ ተመሳሳይ አስተሳሰብ ይገልጻል፣ ግነታዊ ባልሆነ መንገድ (ማለትም፣ "በሕይወቴ ቀኖች ሁሉ፣" መዝ. 23፡6ሀ)።

ደግሞም መዝ. 5፡4ለ ላይ "ክፉ ከያህዌ ጋር አያድርም/አይኖርም፣" የሚለውን ተመልከት፣ ነገር ግን ታማኝ ተከታይ ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ይሻል (መዝ. 61:4፤ 84:10)።

**15፡2-5** እነዚህ ቁጥሮች የሚገልጹት (በአዎንታዊ እና በአሉታዊ በተመዛዘነ መልኩ) ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን ግለሰብ ዓይነት ነው (መዝ. 24፡3-6)።

1. በቅንነት የሚሄድ ("ያለ ነውር፣" ቢ.ዲ.ቢ 1071፣ መዝ. 18:23፣31፤ 119:80፤ ምሳ. 28:18)
2. ጽድቅን የሚያደርግ
3. እውነትን የሚናገር (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 12:1 ላይ) በልቡ
4. የማይሸነግል
5. በባልንጀራው ላይ ክፉ የማያደርግ
6. ዘመዶቹንም የማይሰድብ
7. ኃጢአተኛ በፊቱ የተናቀ
8. እግዚአብሔርን የሚፈሩትን የሚያከብር (ማለትም፣ የኪዳን ባልንጀሮቹን)
9. በእውነት የሚምል (ማለትም፣ መሐላ፣ ሌዋውያን 27)
10. የማይከዳ (ለራሱ ጥቅም መሐላውን የማያጥፍ)
11. በአራጣ የማያበድር (ዘጸ. 22:25፤ ሌዋ. 25:36)
12. በንጹሑ ላይ መማለጃን የማይቀበል (ዘጸ. 23:8፤ ዘዳ. 16:19)

እነዚህ ሁሉ ባሕርያት የሚገልጹት መልካም ሰው እንዴት እንደሚኖርና ከሌሎች ጋር እንዴት እንደሚመላለስ እንደሆነ ተገንዘብ። እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት ሕዝቡን ማክበር ማለት ነው። ታማኝ ተከታዮች ማለት እንዲኖሩና እንዲያፈቅሩ ነው፣ ዓለም ፈጣሪውን እግዚአብሔርን እንዲያውቅና እንዲቀርብ።

**15፡4ለ "እግዚአብሔርን የሚፈሩ"** ይህ ተደጋጋሚ መግለጫ ነው፣ ለታማኝ ተከታዮች (መዝ. 25:12፣14፤ 103:11፣13፤ 118:4)። እነርሱ በብዙ መንገዶች ተገልጸዋል።

1. እነርሱ ያደረጉት
   ሀ. ምስጋና፣ ክብር፣ እና በያህዌ ፊት በፍርሃት መቆም ነው፣ መዝ. 22፡23
   ለ. በእርሱ መንገድ ተራምደዋል፣ መዝ. 128፡1
2. እርሱ ለእነርሱ ያደረገላቸው
   ሀ. ኪዳኑን ገለጸላቸው፣ መዝ. 25፡14
   ለ. ደኅንነትን በቅርብ አመጣላቸው፣ መዝ. 85፡9
   ሐ. ረድኤትና ጋሻቸው ነው፣ መዝ. 115፡11
   መ. ባርኳቸዋል፣ መዝ. 115፡13፤ 128፡1
   ሠ. መሻታቸውን ፈጽሟል፣ መዝ. 145፡19 (ደግሞም "ጩኸታቸውን ይሰማል፣ ያድናቸዋልም")

**15፡5ሐ** ይህ የማጠቃለያ መግለጫ ነው። ከእግዚአብሔር ጋር በኪዳን የሚኖሩት እና የእነርሱ ወንድሞች/እኅቶች ፈጽመው አይናወጡም (ቢ.ዲ.ቢ 556፣ ኬቢ 555፣ ኒፋል ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 17:5፤ 30:6፤ ምሳ. 10:30፤ 12:3)። አእት እርሱን የሚተረጉመው "ዘወትር ደኅንነቱ ይጠበቃል" በሚል ነው። ኢሳይያስ 33፡15 ትይዩ ይመስላል ወደ ያህዌ መቅረብ ለቻሉትና አብረው ለሚኖሩት። እንደዚያ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ኢሳ. 33፡16 ከመዝ. 15፡5ሐ ጋር ትይዩ ነው።

የደኅንነት ዓላማ ግለሰብ-ተኮር ብቻ አይደለም፣ ኅብረተሰባዊ ደግሞ እንጂ ነው! ለእግዚአብሔር ያለ ፍቅር እርስ በርስ መፋቀርን ማመንጨት አለበት! ጽድቅን ከፍትሕ መለያየት ፈጽሞ አይኖርብንም! የዘፍጥረት 3 ውድቀት በሰዎች ሁሉ ላይ ተጽዕኖውን ዐሳርፏል (መዝ. 14:1-3)። የእግዚአብሔር አምሳል (ዘፍ. 1:26-27 በሰዎች ተንድቷል። የሰው ልጅ የሰው ልጅ ወደ ውስጥ ዞሯል። ግለኝነት እና ነፃነት አሁን የእርሱን/እርሷን አስተሳሰብና ድርጊት ባሕርይ ይዟል። አዲሱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ተቃርኖ ይህን ትኩረቱን ቀይሯል (ኤር. 31:31-34፤ ሕዝ. 36:25-27)። አዲሱ ሰው እንደገና ነጻ የመሆን ስሜት አለው። እሱ/እሷ ለእግዚአብሔር/ለሌሎች ይኖራሉ።

◘ **"ፈጽሞ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም መዝ. 9፡5 ላይ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወስን አይደለም።

1. ያህዌን በመቅደስ ሊቀርብ የሚችለውን ሰው ግለጽ።
2. "የሕይወት ስልት እምነት" ከደኅንነት እምነት ጋር እንዴት ይዛመዳል?
3. የታማኝ ትከታይን አምስት አዎንታዊ እና አሉታዊ ባሕርያትን ዘርዝር።
4. "አራጣ አበዳሪን" ግለጽ።
5. ይህ መዝሙር አንድምታው ጻድቅ ሰው ፈጽሞ እንደማይቸገር ነውን?

## መዝሙር 16
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ የመዝሙረኛው ክፍል በሕይወት እና አዳኙ በሞት <br> <u>ኤምቲ መግቢያ</u> <br> "የዳዊት መዝሙር" <br> 16:1-4 | የታማኝ ተስፋ፣ እና የመሢሑ ድል | የግለሰብ እምነት ድርጊት በአምላክ ኃይል ለማዳን (የእምነት መዝሙር) | የእምነት ጸሎት | ያህዌ ውርሴ |
| | 16:1 | 16:1-2 | 16:1-3 | 16:1 |
| | 16:2-3 | | | 16:2-3a |
| | | 16:3-4 | | 16:3b-6 |
| 16:5-6 | 16:4 | | 16:4 | |
| 16:7-11 | 16:5-6 | 16:5-6 | 16:5-6 | |
| | 16:7-8 | 16:7-8 | 16:7-8 | 16:7-8 |
| | 16:9-11 | 16:9-10 | 16:9-10 | 16:9-11 |
| | | 16:11 | 16:11 | |

### **የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 16:1-4**

**[1]አቤቱ፥ በአንተ ታምኛለሁና ጠብቀኝ።**
**[2]እግዚአብሔርን፦ አንተ ጌታዬ ነህ አልሁ**
**ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም።**
**[3]ፈቃድህ ሁሉ በምድር ባሉት ቅዱሳንና ክቡራን ላይ ነው።**
**[4]ወደ ሌላ ለሚፋጠኑት መከራቸው ይበዛል**
**የቍርባናቸውን ደም እኔ አላፈስሰውም፥**
**ስማቸውንም በከንፈሬ አልጠራም።**

**16:1 "አምላኬ ሆይ ጠብቀኝ"** ይህ ብቸኛው ተተኳሪ ነው (ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ ተተኳሪ) መዝሙር 16 ላይ። እሱም አስቸኳይ የጸሎት ጥያቄ ነው። ከመዝ. 16፡10-11 አኳያ መዝሙረኛው ሞት እንደገጠመው ግልጽ ነው። እሱ ሕይወትን ይጠይቃል ነገር ግን ሞት እንኳ ቢሆን ከእግዚአብሔር እንደማይለየው ያውቃል (ሮሜ. 8፡31-38)። እዚህ መዝሙር ላይ መለኮት የሚጠራው

1. ኤል፣ ቁ. 1 (አጠቃላይ የእግዚአብሔር መጠሪያ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ))
2. ያህዌ፣ ቁ.2፣5፣7፣8

3. አዶን፣ ቁ. 2

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች መዝ. 1፡1 ላይ።

▣ ***"ባንተ ታምኛለሁና"*** ይህ የብዙዎቹ መዝሙራት ጭብጥ ነው! ለ "መታመን" መዝ. 5፡11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

ሰዎች በእግዚአብሔር በራሱ መልክና አምሳል የተፈጠሩ ናቸው (ዘፍ. 1፡26-27)። የተፈጠርነው ለኅብረት ነበር (ዘፍ. 3፡8)። ሰላምን፣ ዕረፍትን፣ ደስታን፣ ዓላማን፣ ደኅንነትን ማግኘት የምንችለው በእርሱ ብቻ ነው!

**16፡2** ይህ የመዝሙረኛው የእምነት መግለጫ ነው። ቁጥር 2 ቀደም ሲል የነበረውን ጸሎት ወይም መግለጫ የሚያጠቃልል ይመስላል።

▣

***አአመመቅ*** ***"ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም"***
***አኪጀት*** ***"የእኔ በጎነት ከአንተ ውጭ የለም"***
***አየተመት*** ***"ከአንተ በቀር በጎነት የለኝም"***
***አእቅ*** ***"ያሉኝ በጎ ነገሮች ሁሉ ካንተ ነው የመጡት"***
***የተእመቅ*** ***"ያለኝ መልካም ነገር ሁሉ ካንተ ብቻ ነው የመጣው"***
***አእት መጽሐፍ ቅዱስ*** ***"የመልካምነቴ ብቸኛ ምንጭ"***
***ጄፒኤስኦኤ*** *የግርጌ ማስታወሻ* ***"በጎነት ካንተ ውጭ የለኝም"***

አንዱ ሊፈተን ይችላል፣ ይህንን የአኪ የጽድቅ ዶክትሪን የሆነ ሐረግ ሲያነብ፣ ነገር ግን በብኪ የተሻለው ትይዩ መዝ. 73፡25-28 ነው። ያህዌ የመዝሙረኛው ብቸኛ "በጎነት" ነው። የአሕዛብ ጣዖቶች ሐሰት ናቸው (ዝኪ. ቁ. 3-4)። ባለጸጋው፣ መሐሪው፣ የኪዳን አምላክ በእርሱ የሚያምኑትንና እንደ ኪዳን መስፈርቱ የሚኖሩትን ያከብራቸዋል (ማለትም፣ ብኪ - የሙሴ ኪዳን፤ አኪ - ወንጌል፣ ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝ. 36፡25-27)። ውጤቱም ሕይወት እና ከሕይወት በኋላ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት።

**16፡3-4** ይህንን ቁጥር እንዴት መረዳት እንደሚቻል ብዙ ጥያቄዎች አሉ። የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ስለ እነርሱ የሚለው (ገጽ 1297) "እነዚህ እጅግ ግልጽ ካልሆኑት የመዝሙር ቁጥሮች መካከል ናቸው።"

1. "ቅዱሳን" እነማን ናቸው (ቢዲቢ 872) — ጥቂት ሊቃውንት (አእመቅ፣ አኢመቅ) የመጨረሻዎቹን ቃላት ይወስዳሉ፣ የመዝ. 16፡2 እናም አሉታዊውን ወደ ቁ. 3 ያመጡታል፣ እሱም "ቅዱሳን" "የምድርን ቅዱሳን መናፍስት" እንዲያመለክቱ (ማለትም፣ የመዝ. 16፡4 ጣዖታትን)። ከታች ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።
2. "ባለ ግርማዎቹ" እነማን ናቸው (ቢዲቢ 12) — በትይዩነት ምክንያት እነርሱ አንድም አዎንታዊ (ማለትም፣ መልካሞች፣ አእት) አንድም አሉታዊ ናቸው (የከነአን ጣዖታት፣ አኢመቅ)።

እነዚህን ሁለት መጠሪያዎች የኪዳኑን ሕዝቦች እንደሚጠቅሱ መውሰድ ይቻላል፣ ቁ. 3 ላይ፣ ጣዖት አምላኪ የሆኑትን፣ ቁ. 4 ላይ። በርካታ ትርጉሞች ቁጥር 3 እና 4ን ወደ ተለያዩ አንጓዎች ይለያዩአቸዋል። ጥያቄው፣ "ቁ. 3-4 የሚፈጥረው ተቃርኖ ነው ወይስ የተራዘመ ገለጻ?"

**16፡3 "ቅዱሳን"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል *ቃዶሽ* ነው (ቢዲቢ 872)፣ እሱም ጥቅም ላይ የዋለው

1. የያህዌ ታማኝ ተከታዮች — ዘዳ. 33፡3፤ መዝ. 34፡9፤ ዳን. 8፡24
2. መንፈሳዊ ሕላዌዎች (ማለትም፣ መላእክት) – ኢዮብ 5፡1፤ 15፡15፤ መዝ. 89፡5፣7፤ ዳን. 8፡13 (ሁለቴ)፤ ዘካ. 14፡5

## ልዩ ርዕስ፡ ቅዱስ (שׁדק)

I. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. *kadosh* (BDB 872) የሚለው ቃል *ሥርወ-ቃል* ርግጠኛ አይደለም፣ ምናልባት ከነዓናዊ ይሆናል። ሊሆን የሚችለው ከፊሉ *ሥር* (ማለትም፣*kd)* ፍችው "መከፋፈል" ነው። ይህም የታወቀው ማብራሪያ ምንጭ ነው "መለየት (ከከነዓናውያን ባህል፣ ዘዳ. 7፡6፤ 14፡2፣ 21፤ 26፡19) ለእግዚአብሔር ጥቅም።"
   ለ. እሱም የሚዘመደው ከእግዚአብሔር መገኘት ጋር ነው፣ በነገሮች፣ በታዎች፣ ጊዜያት፣ እና ሰዎች። እሱም በዘፍጥረት ላይ በጥቅም ላይ አልዋለም፣ ግን በዘጸአት፣ ሌዋውያን፣ እና ዘኁልቁ ላይ የተለመደ ነው።
   ሐ. በትንቢታዊ *ሥነ-ጽሑፍ* (በተለይም፣ ኢሳይያስና ሆሴዕ) አካላዊ ነገሩ ቀድሞ የነበረው፣ ግን ወደፊት በተጋነነ መልኩ አይመጣም። እሱም የእግዚአብሔርን ማንነት የሚያሳይ መንገድ ይሆናል (ኢሳ. 6፡3)። እግዚአብሔር ቅዱስ ነው። የእሱ ስም ባሕርዩን የሚወክለው ቅዱስ ነው። የእሱ ሕዝቦች የእሱን ባሕርይ ለተቸገረው ዓለም የሚገልጡት ቅዱሳን ናቸው (ኪዳኑን በእምነት እስከ ታዘዙ ድረስ)።
   መ. የእግዚአብሔር ምሕረትና ፍቅር ከ*ሥነ-መለኮታዊ* ጽንሰ-ሐሳቦች፣ ከኪዳናት፣ ፍትሕ፣ እና ጠቃሚ ባሕርይ የሚለያይ አይደለም። በዚህ ስፍራ ያለው ክርክር እግዚአብሔር ወደ አልተቀደሱት፣ የወደቁት፣ ዐመጸኛ ሰዎች መሆኑ ነው። አስደናቂ የሆነ አንቀጽ አለ፣ እግዚአብሔር እንደ "ምሕረትን የተሞላ" እና እግዚአብሔር እንደ "ቅዱስ" መካከል በRobert B. Girdlestone፣ *Synonyms of the Old Testament*፣ (የብሉይ ኪዳን ተመሳስሎ) ገጽ. 112-113።

II. አዲስ ኪዳን
   ሀ. የአዲስ ኪዳን ጸሐፍት (ከሉቃስ በስተቀር) የዕብራዊ አስተሳሰበኞች ናቸው፣ ግን የኮኔ ግሪክ ተጽዕኖ አለባቸው (ማለትም ሴፕቱዋጂንት)። እሱም የግሪክ የብኪ ትርጉም ነው እንጂ የጥንታዊ ግሪክ *ሥነ-ጽሑፍ*፣ አስተሳሰብ፣ ወይም ሙዳየ ቃላታቸውን የሚቆጣጠር አይደለም።

ለ. ኢየሱስ ቅዱስ ነው፣ ምክንያቱም እሱ የእግዚአብሔር እና እንደ እግዚአብሔር ስለሆነ (ሉቃስ 1:35፤ 4:34፤ ሐዋ. 3:14፤ 4:27፣30)። እሱ ቅዱሱና ጻድቁ ነው (ሐዋ. 3:14፤ 22:14)። ኢየሱስ ቅዱስ ነው፣ ምክንያቱም ኃጢአት የሌለበት ስለሆነ (ዮሐንስ 8:46፤ 2ቆሮ. 5:21፤ ዕብ. 4:15፤ 7:26፤ 1ጴጥ. 1:19፤ 2:22፤ 1ዮሐንስ 3:5)።
ሐ. እግዚአብሔር ቅዱስ ስለሆነ፣ ልጆቹም ቅዱሳን መሆን አለባቸው (ሌዋ. 11:44-45፤ 19:2፤ 20:7፣26፤ ማቴ. 5:48፤ 1ጴጥ. 1:16)። ኢየሱስ ቅዱስ ስለሆነ፣ ተከታዮቹም ቅዱሳን መሆን ይገባቸዋል (ሮሜ. 8:28-29፤ 2ቆሮ. 3:18፤ ገላ. 4:19፤ ኤፌ. 1:4፤ 1 ተሰ. 3:13፤ 4:3፤ 1ጴጥ. 1:15)። ክርስቲያኖች የዳኑት ክርስቶስን በመምሰል እንዲያገለግሉ ነው (ቅድስና)።

**16:4**
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመት** | **"ኀዘን"** |
| **አእቅ** | **"ችግር"** |
| **አኢመቅ** | **"በርካታ ጣዖታት"** |
| **LXX** | **"ደካማነት"** |
| **የተእመቅ** | **"በርካታ ችግር"** |

"ችግር" የሚለው ቃል (עצבות፣ ቢዲቢ 781) "ከጣዖታት" ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው (עצבים፣ ቢዲቢ 781፣ አኢመቅ)። ዐውደ-ጽሑፉ ስለ ጣዖት አምልኮ መሆኑ ግልጽ ነው። ማን በትክክል እንደተጠቀሰ ርግጠኝነት የለውም ቁ. 3 ላይ።

"ሌላው" የሚለውን ቃል መመልከት ይቻላል (אחר፣ ቢዲቢ 29 I፣ ቁ. 4) እንደ "ሌሎች ጣዖታት" אחרים ፣ ኢሳ. 42:8፤ አእት መጽሐፍ ቅዱስ ገጽ 866፣ ቁ. 29)።

ለተብራራ ገለጻ ኒዶቲ ቅጽ 2፣ ቁ. 860-862 ወይም ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ ገጽ 141-142 ተመልከት።

▣ መዝሙረኛው በያህዌ የታመነው እምቢ ያለው
1. የቊርባን ደም ላለማፍሰስ (የእንሰሳት መሥዋዕት ወይም የወይን ዘይቤ)
2. ስማቸውን በከንፈሩ ላለመጥራት (ዘጸ. 20፡3-5)

**መዝሙር ፡ 16፡5-6**
**[5]እግዚአብሔር የርስቴ እድል ፈንታና ጽዋዬ ነው፥**
**ዕጣዬንም የምታጠና አንተ ነህ።**
**[6]ገመድ ባማረ ስፍራ ወደቀችልኝ፥**
**ርስቴም ተዋበችልኝ።**

**16፡5-6** ቁጥር 4 ላይ የተጠቀሰውን የመጠጥ ቊርባን "ጽዋ" የሚለውን የመዝሙረኛውን የ "ጽዋ" ፈሊጣዊ አባባል ያስታውሳል፣ እሱም የአንዱን ዕጣ-ፈንታ የሚገልጽ (መዝ. 11:6፤ 23:5፤ 75:8፤ 116:13)። እሱ ዘወትር አሉታዊ ፍች ነው የሚኖረው፣ እዚህ ግን አይደለም።

"ዕጣ" የሚጠቅሰው የከነዓንን ምድር ለነገዶች ይዞታ በዕጣ መከፋፈል ነው፣፣ በኢያሱ አማካኝነት (ኢያሱ 13-19)፣ እሱም ያህዌ ለአብርሃም የገባውን ተስፋ ትንቢታዊ ፍጻሜ ያገኘበት (ዘፍ. 12፡1-3)። ሌዋውያንና ካህናት 48 ከተሞችን ብቻ ነው የወረሱት (ኢያሱ 20-24)። እነርሱ የተባለላቸው ጌታ ራሱ ርስታቸው እንደሆነ ነው (ዘኊ. 18፡20፤ ዘዳ. 18፡1)። ሆኖም፣ መዝሙር ላይ ይህ መለያ ወደ ሁሉም ታማኝ ተከታዮች ተስፋፍቷል (መዝ. 73:26፤ 119:57፤ 142:5፤ ደግሞም ሰቆ.. 3:24)።

ቁጥር 6 ይሄንን ምናብ ይቀጥላል "ገመድ ወደቀችልኝ" በሚል። መዝሙረኛው የሚያስረግጠው ርስቱ የተዋበ እንደሆነ ነው (ማለትም፣ ኤር. 3፡19)።

**መዝሙር ፡ 16፡7-11**
**[7]የመከረኝን እግዚአብሔርን እባርካለሁ**
**ደግሞም በሌሊት ኵላሊቶቼ ይገሥጹኛል።**
**[8]ሁልጊዜ እግዚአብሔርን በፊቴ አየዋለሁ**
**በቀኜ ነውና አልታወክም።**
**[9]ስለዚህ ልቤን ደስ አለው ምላሴም ሐሴት አደረገች**
**ሥጋዬም ደግሞ በተስፋ ታድራለች**
**[10]ነፍሴን በሲኦል አትተዋትምና፥**

ቅዱስህንም መበስበስን ያይ ዘንድ አትተወውም።
"የሕይወትን መንገድ አሳየኸኝ
ከፊትህ ጋር ደስታን አጠገብኸኝ፥
በቀኝህም የዘላለም ፍሥሐ አለ።

**16፡7-11** መዝሙረኛው እምነቱን የሚጥለው በያህዌ
1. ምክር፣ ቁ. 7ሀ (መዝ. 32፡8)
2. ተግሣጽ፣ ቁ. 7ለ
3. ጽኑ መገኘት፣ ቁ. 8፣ 11
4. ድል፣ ቁ. 8ለ

በውጤቱም በያህዌ ባለው ደኅንነት መደሰቱ ነው (ዝኪ. ቁ. 9)፣ ሞት እንኳ ቢሆን (ቁ. 10-11)።
1. እሱ መዝሙረኛውን በሲኦል አይተወውም፣ ቁ. 10 (ኢዮብ 14:14-15፤ 19:25-27)
2. እሱም የሕይወትን መንገድ ያሳውቀዋል (መዝ. 139:24፤ ምሳ. 15:24፤ ማለትም፣ በየቀኑ ለሆነ የታማኝነት ኑሮ፤ ለተመሳሳይ ሐረግ መዝ. 101፡2፣6 ተመልከት)
3. እሱም በግሉ በሲኦል እንኳ አብሮት ይሆናል (መዝ. 139፡7-8)
4. እሱም መዝሙረኛው የሚያስፈልገውን ሁሉ አትረፍርፎ ይሰጠዋል

በመከራ ጊዜያት እንኳ ታማኝ ተከታዮች ያህዌ ከእርሱ/እርሷ፣ ለእርሱ/ለእርሷ መሆኑን ሊያውቁ ይችላሉ፣ እናም ፈጽሞ አይተወውም/አይተዋትም! ይህ በያህዌ ታማኝነት ላይ ያለን እምነት ተስፋችን፣ ደስታችን፣ ሰላማችን፣ ዕረፍታችን፣ እና ድላችን ነው!

**16፡8ለ "በቀኜ ነው"** የያህዌ ቀኝ እጅ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አምላክ እንደ ሰው ሲገለጽ [ሰውኛነት] መዝ. 2፡4-6)። ቀኝ እጅ ለኃይልና ለብርታት ምሳሌ ነው። መሲሑ በእግዚአብሔር ቀኝ እንደተቀመጠ ተገልጿል፣ ይኸውም የኃይልን፣ ልዕልናን፣ እና ሥልጣንን የሚገልጽ።

በዚህ መዝሙር ላይ የብዙ ነገሮች ውኅደት መሲሐዊ ያደርገዋል፣ ለሐዋርያት፣ ጴጥሮስ እና ጳውሎስ
1. ቀኝ እጅ ምናባዊ፣ ቁ. 8፣ 11
2. ከሥጋዊ ሕላዌ ባለፈ ሕይወት
3. መጠሪያው "ቅዱሱ"

ቁጥር 10 ላይ ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት።

**16:9**
**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"ክብሬ"**
**አየተመት፣ አኢመቅ** **"ነፍሴ"**
**LXX** **"አንደበቴ"**
**ጀፒኤስኦኤ** **"መላ ሕልውናዬ"**
**የተእመቅ** **"መንፈሴ"**

"ክብር" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል (יכבוד፣ ቢዲቢ 458 II) የጸሐፊ ስሕተት ሊሆን ይችላል፣ ለ"ሊቨር" (כבד፣ ቢዲቢ 458፣ ዘፍ. 49፡6፤ መዝ. 30፡12)፣ እሱም እንደ ልብ፣ የሰውን ሁለንታዊ ይገልጻል (ኒዶቲ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 587-588፤ አእት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 866፣ ቁ. 11)። "ልብ፣" "ሊቨርr/ክብር፣" እና "ሥጋ" ሁሉም ትይዩ መሆናቸውንና ራሱን መዝሙረኛውን እንደሚገልጹ ተገንዘብ።

**16:10**
**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"ቅዱስህ"**
**አየተመት፣ ጀፒኤስኦኤ** **"ታማኝህ"**
**አኢመቅ፣ የተእመቅ** **"ታማኝ አገልጋይህ"**
**LXX** **"አገልጋይህ"**
**አእትመጽሐፍ ቅዱስ** **"ታማኝ ተከታይህ"**

ዕብራይስጡ "መልካምህ" የሚል አለው (חסיד፣ ቢዲቢ 339)። ይህ ቃል ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው፣ እነዚያን የኪዳኑን ሕዝቦች ለመግለጽ፣ ያህዌን የሚወዱትን፣ የሚያገለግሉትን፣ እና የሚታዘዙትን (መዝ. 4:3፤ 12:2፤ 32:6፤ 86:2፤ ሚክያስ 7:2)። ለያህዌ አጠቃቀም ላይ ሲውል የሚተረጎመው "ደግ" (መዝ. 18:25፤ 145:17) ወይም "ቸር" በሚል ነው (ኤር. 3:12)።

ይህ ቁጥር በሁለቱም በመጠቀሱ ምክንያት፣ በጴጥሮስ (ሐዋ. 2፡27፣31) እና በጳውሎስ (ሐዋ. 13፡35) የኢየሱስን ትንሣኤ ለመጥቀስ፣ በዚህ መዝሙር ላይ ቃሉ የተተረጎመው "ቅዱሱ" በሚል ነው (አአመመቅ፣ አኪጀት)። እኔ ርግጠኛ አይደለሁም፣ ይህንን ቁጥር በመዝሙር 16 እንዴት መመልከት እንደሚቻል። ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ እሱ በግልጽ የሚጠቅሰው መልካም፣ ታማኝ እስራኤላውያንን ነው(የቁ. 10ን ትይዩነት ተገንዘብ)። እንግዲያውስ እሱ በሐዋርያው መረዳት አግኝቶ የነበረው እንደ
1. ትንቢታዊ
2. ዐቢይ ምድባዊ

3. ብዝኃ ተፈጻሚነት

ሐዋርያት ወደ ኋላ ወደ ብኪ ተመልክተው፣ በርካታ ምልክቶችን እና ንግር (ጥላ)፣ ብሎም የተለዩ ትንበያዎችን አይተዋል፣ ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ሥራ፣ ሞት፣ ትንሣኤ፣ እና ዳግም ምጽአት! እኔ የእነርሱን ተመስጦ አምናለሁ።

▣

**አአመመቅ፣ የተእመቅ** **"ጥልቁ"**
**አኪጀት፣ LXX** **"መበስበስ"**
**አየተመት፣ ጀፒኤስአኤ** **"ጥልቁ"**
**አኢመቅ** **"ጥልቁ"**

ኤምቲ "ጥልቅ" አለው (ቢዲቢ 1001) እሱም ከሲኦል ጋር ትይዩ ነው (ኢዮብ 33:18፤ ኢሳ. 38:17-18)። ለሲኦል ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው? መዝ. 1፡6 ላይ፣ እንዲሁም መዝ. 6፡5፤ 9፡13 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት። ሁለቱም ሞትን መጥቀሻ መንገዶች ናቸው።

LXX በሁለቱም ተጠቅሷል፣ በጴጥሮስ እና ጳውሎስ ሐዋርያት ሥራ ላይ፣ የኢየሱስን ትንሣኤ ለማስረገጥ። በርካታ ቦታዎች ብኪ ላይ ይገኛሉ፣ ትንሣኤን የሚያስረግጡ፣ ቢያንስ ፍንጭ የሚሰጡ (ኢዮብ 14:14-15፤ 19:25-27፤ መዝ. 17:15፤ 49:15፤ 56:13፤ 73:24፣25፤ 86:13፤ ኢሳ. 26:19፤ ዳን. 12:2)። ሕዝቅኤል 37 የሕዝቦችን መመለስ የሚያመለክት ይመስላል፣ የግለሰብን ትንሣኤ ሳይሆን።

እግዚአብሔር ይመስገን፣ ስለ ሙሉው የአኪ መገለጥ።

1. የኢየሱስ ባዶ መቃብር እና ድኅረ-ትንሣኤ መታየት
2. የጳውሎስ የትንሣኤ ማብራሪያ፣ 1 ቆሮንቶስ 15 ላይ

ከሕይወት ወዲያ ቀጣይነት ያለው መገለጥ ነው!

የኢየሱስ ሕይወት፣ ትምህርት፣ ሞት፣ እና ትንሣኤ የሐዋርያትን ርዕዮተ-ዓለም ቀየረው። የእነርሱ የብኪ አመለካከት ተሻሻለ። እነርሱ ብኪን መፈለግ ጀመሩ፣ ለትንቢቶች፣ ለአጠቃላይ ምድቦች፣ እና ለዚህ አዲስ እውነታ ፍንጭ። ኢየሱስ ራሱ ነው ይሄንን የጀመረው፣ ስለ ራሱ የማብራሪያ ትርጓሜዎች፣ ከብኪ፣ ለሁለቱ የኢማሆስ መንገድ ደቀ-መዛሙርት፣ እነርሱም ከቡድኑ ጋር የነበሩ፣ በደርቡ ክፍል (ሉቃስ 24፡25-27)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "ቅዱሳን" የሚለውን ቃል ግለጽ።
2. "ቅዱሳን" እንደ "ባለ ግርማ" አንድ ዓይነት ናቸውን?
3. ቁጥር 4 እንዴት ከጣዖት አምልኮ ጋር ይያያዛል?
4. "ክፍል" የሚለውን ቃል የብኪ አጠቃቀም ግለጽ።
   እሱስ ከ "ዕጣ" ጋር ትይዩ ነውን?
5. የትኛው የሰው አካል ብልት ነው የሐሳብና የስሜት መገኛ ነው ተብሎ የሚታመነው?
6. ይህ መሢሐዊ መዝሙር ነውን፣ ቁጥር 10 ሐዋርያት ሥራ ላይ በመጠቀሱ ምክንያት?
7. መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ለምን እንደ "መንገድ" ይገለጻል?

## መዝሙር 17
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ከጨቋኝ ለመጠበቅ ጸሎት ኤምቲ መግቢያ "የዳዊት ጸሎት" | የእምነት ጸሎት ለፍጻሜው ደኅንነት | ከግል ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት (ሰቆቃ) | የንጹሕ ሰው ጸሎት | የንጹሕ ልመና |
| 17:1-5 | | | | |
| | 17:1-2 | 17:1-2 | 17:1-2 | 17:1-2 |
| | 17:3-5 | 17:3-5 | 17:3-5 | 17:3-4ሀ |
| | | | | 17:4ለ-7 |
| 17:6-12 | | | | |
| | 17:6-9 | 17:6-7 | 17:6-7 | |
| | | 17:8-12 | 17:8-9ሀ | 17:8-12 |
| | | | 17:9ለ-12 | |
| | 17:10-12 | | | |
| 17:13-15 | | | | |
| | 17:13-14 | 17:13-14 | 17:13-14 | 17:13-14ለ |
| | | | | 17:14ሐ-15 |
| | 17:15 | 17:15 | 17:15 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 17:1-5**

**1 አቤቱ፥ ጽድቄን ስማ ጩኸቴንም አድምጥ**
**በተንኰለኛም ከንፈር ያልሆነውን ጸሎቴን አድምጥ።**
**2 ፍርዴ ከፊትህ ይውጣ፥**
**ዓይኖችህም በቅንነት ይዩ።**
**3 ልቤን ፈተንኸው**
**በሌሊትም ጐበኘኸኝ**
**ፈተንኸኝ፥ ምንም አላገኘህብኝም።**
**4 የሰውን ሥራ አፌ እንዳይናገር ፈቃዴ ነው**
**ስለ ከንፈሮችህ ቃል ጭንቅ የሆኑ መንገዶችን ጠበቅሁ።**
**5 እግሮች እንዳይናወጡ**
**አረማመዴን በመንገድህ አጽና።**

**17፡1** ትይዩዎቹ ተተኳሪዎች የመዝሙረኛውን ጸሎት እንደሚያመለክቱ ተገንዘብ።

1. ስማ – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ ተተኳሪ፣ መዝ. 17:6፤ 27:7፤ 28:2፤ 30:10፤ 39:12፤ 54:12፤ 61:1፤ 64:1፤ 84:8፤ 102:1፤ 119:149፤ 130:2፤ 143:1
2. አድምጥ – ቢዲቢ 904፣ ኬቢ 1151፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ መዝ. 5:2፤ 55:2፤ 61:1፤ 86:6፤ 142:6
3. አድምጥ – ቢዲቢ 23፣ ኬቢ 27፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ መዝ. 5:1፤ 39:12፤ 49:1፤ 54:2፤ 55:1፤ 77:1፤ 80:1፤ 84:8፤ 140:6፤ 141:1፤ 143:1

መዝሙር የእግዚአብሔር ሕዝብ መጽሐፍ ነው፣ እሱ እንዲያደምጥ በቅንነት የሚጠይቅ (ማለትም፣ ተመልክቶ ምላሽ እንዲሰጥ) የእነርሱን ሁነኛ መሻት።

ቁጥር 1 ላይ ትክክለኛ ምክንያት ያለውን የሚገልጹ ቃላት (ቢዲቢ 841) "ሐሰተኛ ከንፈር" ካለው ጋር ተቃርነዋል (ኢሳ. 29፡13)።

መዝሙር 17፡1 ከ 17፡6 ጋር ትይዩ ነው። የዚህ መዝሙር ሦስቱም አንጓዎች ሁሉ የሚጀምሩት በበርካታ ተተኳሪዎች ነው፣ በመዝሙረኛው አኳያ እንዲሠራ እግዚአብሔርን የሚለምኑ!

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ከሐሰተኛ ከንፈር ያልሆነ"** |
| **አየተመት፣ አኢመቅ** | **"ከሐሰት ነጻ ከሆነ ከንፈር"** |
| **አእቅ** | **"ንጹሕ ጸሎት"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ከተንኮል ያልሆነ"** |

መዝሙረኛው ቅንነቱን ያስረግጣል። እሱም የሚጸልየው ከተሸሸገ ሐሳብ ወይም ከሚታወቅ ውሸት አኳያ አይደለም (ኢሳ. 29፡13)።

**17፡2** ቁጥር አንድ፣ ሦስት ተተኳሪዎች እንዳሉት ሁሉ፣ ይህ ሡጥር ሁለት ግልጽ የሆኑ ተጽዕኖዎች አሉት።

1. ፍርዱ/ጽድቁ ከአንተ ዘንድ ይምጣ — ቢዲቢ 422፣ ኬቢ 425፣ ያልተጠናቀቀ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ዓይንህ በፍትሓዊነት ትመልከተኝ — ቢዲቢ 302፣ ኬቢ 301፣ ያልተጠናቀቀ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ፍትሐዊነት"** |
| **አኪጀት** | **"ቅን"** |
| **አየተመት** | **"ቅን"** |
| **አኢመቅ፣ አእቅ፣** | |
| **ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ** | **"ቅን"** |
| **LXX** | **"ቀናነት"** |

ኤምቲ "ሚዛናዊነት፣" ወይም "ቀናነት" የሚል አለው (ቢዲቢ 449)። እዚህ የሚጠቅሰው ያህዌ በፍትሐዊነት ወይም ባለማዳላት እንደሚፈርድ ነው። መዝሙረኛው እግዚአብሔርን የሚጠይቀው ፍትሐዊ ፍርድ እንዲሰጥ ነው (ዝከ. ቁ. 1ሀ)።

**17፡3-5** መዝሙረኛው ይቆጥራል ለምን እግዚአብሔር እንደሚፈርድለት/እንደሚወስንለት።

1. እግዚአብሔር ምን እንዳደረገለት (ሁሉም የተጠናቀቁ)
   ሀ. ልቡን ፈትኖታል፣ ቁ. 3ሀ
   ለ. በሌሊት ጎብኝቶታል፣ ቁ. 3ለ (ሀ እና ለ ትይዩ ናቸው፣ ያለምንም ይሁንታዊ ልዩነት)
   ሐ. ፈትኖት ምንም አላገኘበትም፣ ቁ. 3ሐ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ ይፈትናል፣ 11፡4ለ ላይ)
2. እሱ ምን እንዳደረገ ወይም እንዳላደረገ
   ሀ. እሱ በአንደበቱ አልተላለፈም፣ ቁ. 3መ
   ለ. ከዐመጽ መንገድ ርቋል (ቃሉ፣ ቢዲቢ 829፣ ፍችው "ዘራፊ፣" ኤር. 7፡11፣ ነገር ግን "ዓመጸኛ" ሊል ይችላል፣ ሕዝ. 18፡10)፣ ቁ. 4
   ሐ. የእግዚአብሔርን መንገድ ተራምዷል፣ ቁ. 5ሀ
   መ. አልተንሸራተተም፣ ቁ. 5ለ (መዝ. 18፡36)

የ "መንገድ" ጽንሰ-ሐሳብ ፍችው፣ መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን የኪዳን ምሪት በጥንቃቄ መከተሉን ነው (መዝ. 37:31፤ 40:2፤ 44:18፤ 66:9፤ 73:2፤ 119:105፤ ምሳ. 14:15)። ክፉ ሰዎች

1. ከመንገድ ያፈነግጣሉ፣ ወደ ቀኝ ወይም ወደ ግራ
2. በመንገድ ይሰናከላሉ
3. አንሸራታች ዳጥ አለባቸው

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር የራሱን ሕዝብ ይፈትናል መዝ. 11፡4ለ-5

**17፡3መ** የዩቢኤስ ጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 182-183) መልካም አጭር ማስታወሻ አለው፣ ይሄንን የቅኔ ስንኝ ለመተርጎም አማራጮች።

“ካጠ፤ እንደ ያልተወሰነ ውቅር ከኋላ ቅጥያ ጋር የተተረጎመ ከሆነ፣ የቁ. 3 የመጨረሻ ክፍል መተርጎም የሚኖርበት እንደ ‘ዕቅዴ (ሐሳቤ) ከአንደበቴ ውጭ አይሄድም’ በሚል ነው (ማለትም፣ ሐሳቤ ከቃሌ ጋር ይሄዳል፣ ቃሌም ሐሳቤን ያስረግጣል)። ፐካጠ በአንደኛ መደብ ነጠላ ግሥ ከተተረጎመ፣ ሐረጉ መተርጎም የሚኖርበት እንደ ‘አድርጌ ብሆን (አንድ ነገር) (ማለትም፣ ክፉ ነገር)፣ (ይህ) በአፌ አያልፍም።”

ደግሞም ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 1112 ተመልከት፣ ለተመሳሳይ የዕርማት ሐሳብ። በኤምቲ ያለው ለውጥ፣ ከ“ክፋቴ” (ቢዲቢ 273፣ ኬቢ 273) ወደ “ተገንዘቤዋለሁ” ወይም “ዐቅጄዋለሁ” (ቢዲቢ 273፣ ኬቢ 273፣ የተጠናቀቀ) የሚያካትተው የአናባቢዎችን ለውጥ ብቻ ነው።

**መዝሙር ፡ 17፡6-12**

> [6]**አቤቱ፥ ሰምተኸኛልና ወደ አንተ ጠራሁ**
> **ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፥ ቃሌንም ስማ።**
> [7]**የሚያምኑህን ከሚቃወሙ በቀኝህ የምታድናቸው፥**
> **ቸርነትህን ድንቅ አድርገህ ግለጠው።**
> [8]**እንደ ዓይን ብሌን ጠብቀኝ፥**
> **በክንፎችህ ጥላ ሰውረኝ፥**
> [9]**ከሚያስጨንቁኝ ከኃጢአተኞች፥**
> **ነፍሴንም ከሚከብቡአት ከጠላቶቼ።**
> [10]**አንጀታቸውን በስብ ቋጠሩ፥**
> **በአፋቸውም ትንቢትን ተናገሩ።**
> [11]**አሁንም እርምጃችንን ከበቡ**
> **ዓይናቸውን ወደ ምድር ዝቅ ዝቅ አደረጉ።**
> [12]**እርሱ ንጥቂያን እንደሚናፍቅ አንበሳ**
> **ተሸኍጦም እንደሚኖር እንደ አንበሳ ደቦል ነው።**

**17፡6-12** ይህ አንጓ የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ድርጊት ነው፣ በመዝሙረኛው እና በእርሱ ጠላቶች ድርጊቶች ላይ።

1. የእግዚአብሔር ድርጊቶች
   ሀ. እርሱ ተጣራ እና እግዚአብሔር መለሰ፣ ቁ. 6
   ለ. እግዚአብሔር የኪዳኑን ፍቅርና ታማኝነት አሳየ (ማለትም፣ ቸርነት፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7 ላይ)
   ሐ. እግዚአብሔር መጠጊያ ሰጠው (መዝ. 5፡11 ላይ ማስታወሻ ተመልከት)
   መ. እግዚአብሔር ጠበቀ/ከለለ “የዓይኔ ብሌን” (ለአንዱ የሚደረግ ፍጹም ጥበቃ ፈሊጥ፣ በተለይም የቅርብ፣ ዘዳ. 32፡ 16፤ ምሳ. 7፡2)
   ሠ. እግዚአብሔር በክንፎቹ ጥላ ከለለው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡11-12 ላይ)
2. የተቃዋሚው ድርጊቶች
   ሀ. እሱን አበላሽተውታል (ማለትም፣ ገድለውታል)፣ ቁ. 9
   ለ. እሱን ከብበውታል፣ ቁ. 9ለ፣ 11ሀ
   ሐ. እነርሱ ልባቸውን ዘግተዋል (“በስባቸው[ቢዲቢ 316] ሸፈኑ” [ቢዲቢ 688፣ ኬቢ 742፣ የተጠናቀቀ]፣” LXX፤ “ስብ” በአሉታዊ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፣ ለሰዎች፣ መዝ. 73፡3 እና 119፡70)
   መ. በእርሱ ላይ በኩራት ይናገራሉ
   ሠ. ዓይናቸውን በእርሱ ላይ አኑረዋል
   ረ. እንደ አንበሳ ቀዳደዱት፣ ቁ. 12

እንዴት የሰላ ተቃርኖ ነው!

**17:6**

**አአመመቅ፣ አኪጀት** **“ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል”**

**አእቅ፣ አኪመቅ፣**

**ጀፒኤስአኤ** **“ጆሮህን ወደ እኔ አዙር”**

ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ እሱም በጸሎት ጥቅም ላይ በሚውልበት ጊዜ፣ ያህዌን ይጠይቃል እንዲዞር/እንዲያዘነብል (2 ነገ. 19:16፤ ኢሳ. 37:17፤ ዳን. 9:18፤ መዝ. 31:2፤ 71:2፤ 86:1፤ 88:2፤ 102:2፤ 116:2)።

ያህዌ፣ ምንም እንኳ ሥጋዊ ያልሆነ መንፈሳዊ ሕላዌ ቢሆንም፣ በሰዎች ቃል ተገልጿል። ልዩ ርዕስ ተመልከት ሰዋዊነት መዝ. 2፡4-6 ላይ። ሰዎች ምንም ቃል የላቸውም፣ ነገር ግን ከዚህ ዓለምና ከእነርሱ ሥጋዊነት ጋር ከሚዛመድ በቀር። የሰዎች ቃል ለእግዚአብሔር ወይም ለመንፈሳዊው ዓለም ጥቅም ላይ የዋለው ዘወትር ዘይቤአዊ ነው።

**17፡7** ይህ ቁጥር ተለጣጣቂ የሆኑ ኃይለኛ፣ ስሜታዊ ሥነ-መለኮታዊ ቃላት ይዟል፣ ከያህዌህ አካልና ምሕረት ጋር የተያያዙ።

1. በድንቅ የተገለጠ — ቢዲቢ 811፣ ኬቢ 930፣ ተተኳሪ (ተመሳሳዩን ቃል ተመልከት ቢዲቢ 810 መዝ. 33፡22፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9፡1 ላይ)
2. ቸርነት፣ የያህዌ ሄሰድ — ቢዲቢ 338 (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7 ላይ) ይኸውም የእርሱን የኪዳን ታማኝነት እና ጽኑ ፍቅር የሚገልጽ
3. አዳኝ ሆይ — ቢዲቢ 446፣ አንቀጽ፣ ማለትም የሚያድን፣ መዝ. 106፡7፣21
4. መታመኛ — ቢዲቢ 340፣ አንቀጽ፣ ያህዌ ጠንካራና ብርቱ መሸሸጊያ ነው፣ በእርሱ ለሚታመኑት፣ መዝ. 5፡11፤ 18፡2

◘ **"በቀኝህ"** ይህንን ሐረግ በብዙ መልኩ መረዳት ይቻላል።
1. ወደ ያህዌ የቀረበ ስፍራ፣ ችግረኛ መጠጊያ የሚያገኝበት፣ አአመመቅ፣ አእት
2. ያህዌ ችግረኛን የሚያድንበት መንገድ (ማለትም፣ የእርሱ ብርቱ ቀኝ እጅ፣ አኪጀት፣ ጄፒኤስኦኤ፣ የተእመቅ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: እጅ መዝ. 7:3-4 ላይ)
3. የቀረበ ግንኙነት፣ በመዝሙረኛውና በጠላቶቹ መካከል (ማለትም፣ የቀረበ ግንኙነት፣ አየተመት)

**17፡9 "ኃጢአተኞች"** ይሄንን ቡድን ለመለየት ያስቸግራል። እሱም ሊያመለክት የሚችለው
1. የኪዳን ባልንጀሮች ለራሳቸው ዓላማ መዝሙረኛውን የሚያጠቁ
2. የኪዳን ባልንጀሮች ሆን ብለው የያህዌን ኪዳን የሚጥሱ
3. የአካባቢው ሕዝቦች፣ እነርሱም ባለማወቅ፣ በጭፍን ጣዖታትን የሚከተሉ፣ ያህዌን ሳይሆን

የመዝሙሩ ዐውደ-ጽሑፍ ብቻ እና ተናጠላዊዎቹ አንጓዎች ናቸው ለመለየት ሊረዱ የሚችሉት። እኔ ርግጠኛ አይደለሁም፣ "ኃጢአተኞች" እንደዛ መሆናቸውን መረዳታቸውን። እነርሱ ዘወትር በድርጊታቸው እግዚአብሔርን እንደሚያገለግሉ ነው የሚያስቡት።

እዚህ መዝሙር ላይ እነርሱ ባለጠጋ፣ ስኬታማ እስራኤላውያን ይመስላሉ፣ ያላቸው ሀብት እና ልጆች እግዚአብሔር እንደተቀበላቸው የኪዳን ምልክት እንደሆነ።

**17፡11 "አሁንም ከብበውናል"** ኤምቲ ግሥ አለው (ቢዲቢ 685፣ ኬቢ 738) እንደ ነጠላ ቁጥር ግን እሱ ከቀጣዩ ስንኝ ጋር ትይዩ ነው፣ በብዙ ቁጥር ግሥ። ስለዚህ፣ ማሶረቲካዊ ሊቃውንት የኅዳግ ማስታወሻ አኑረዋል (*ቁሪ*) እንደ ብዙ ቁጥር እንዲነበብ በማሳሰብ (አአመመቅ "እኛን" ቁ. 11፣ ስንኝ *ሀ* እና *ለ*)።

እንደማስበው ነጠላ ቁጥሩ (ኤምቲ) የተሻለ ነው። ይህ መዝሙር ግለሰባዊ ሰቆቃ ነው፣ ኋላ ግን እንደ አምልኮ ደንብ በሁሉም ማኅበረሰብ ጥቅም ላይ ይውላል፣ ይኸውም መዝሙራት ላይ እጅግ የተለመደ።

◘

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ርምጃችንን"** |
| **አየተመት** | **"ርምጃዬን ተጫኑ"** |
| **አኢመቅ** | **"ቀድመዋል"** |

የዕብራይስጡ ቁ. 11 "ርምጃችንን" በሚል ይጀምራል (ቢዲቢ 81፣ የአንስታይ ብዙ፣ יְנוּשְׁאַ) ነገር ግን አናባቢዎቹን በመቀየር፣ "መቅደም" የሚለውን ግሥ ይሆናሉ (ቢዲቢ 80፣ 80፣ רשׁא ) እሱን በአንድ የዕብራይስጥ የእጅ ጽሑፍ ላይ ያለ፣ አየተመት፣ አኢመቅ።

◘

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ወደ ምድር ዝቅ ሊያደርጉን"** |
| **አኪጀት** | **"ወደ ምድር ሊያጎብጡ"** |
| **አየተመት** | **"ወደ ምድር ሊጥሉኝ"** |
| **አእቅ** | **"ወደ ምድር ሊጎትቱኝ"** |
| **አኢመቅ** | **"ወደ ምድር ሊወረውሩኝ"** |
| **LXX** | **"ወደ ምድር ሊያጎብጡኝ"** |
| **ፔሺታ** | **"በምድር ሊቀብሩኝ"** |

"መጣል" የሚለው ግሣዊ (ቃል ያልተወሰነ አወቃቀር) በጥሬው "ማዘንበል" የሚል ግሥ ነው (ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692) ቁ. 6 ላይ ጥቅም ላይ የዋለ፣ እዚህ ግን ያ ትርጉም ከዐውደ-ጽሑፉ ጋር አይገጥምም። ቃላት ፍች የሚኖራቸው በዐውደ-ጽሑፍ ብቻ መሆኑን አስታውስ! ቅኔ ቃላትን ያስገድዳቸዋል፣ በተለየ መንገድ ጥቅም ላይ እንዲውሉ።

**መዝሙር ፡ 17፡13-15**

**[13]አቤቱ፥ ተነሥ ቀድመህ ወደ ታች ጣለው**
**ነፍሴን ከኃጢአተኛ በሰይፍህ አድናት።**
**[14]አቤቱ፥ ከሰዎች፥ እድል ፈንታቸው በሕይወታቸው ከሆነች**

**ከዚህ ዓለም ሰዎች በእጅህ አድነኝ**
**ከሰወርኸው መዝገብህ ሆዳቸውን አጠግብህ**
**ልጆቻቸው ብዙ ናቸው**
**የተረፋቸውንም ለሕፃናቶቻቸው ያተርፋሉ።**
**[15]እኔ ግን በጽድቅ ፊትህን አያለሁ**
**ክብርህን ሳይ እጠግባለሁ።**

**17፡13-15** መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር ጥሪ ያቀርባል፣ በእርሱ በኩል እንዲሠራ (ቁ. 13)።
1. ተነሥ – ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ ቃል ተተኳሪ
2. ግጠም – ቢዲቢ 869፣ ኬቢ 1068፣ ፔል ተተኳሪ
3. ጣለው – ቢዲቢ 502፣ ኬቢ 499፣ ሂፊል ተተኳሪ
4. አድን – ቢዲቢ 812፣ ኬቢ 930፣ ፔል ተተኳሪ

"ከየቶቹን" ተገንዘብ፣ የጠላቶቹን ባሕርያት (ቁ. 13ለ-14)።
1. ከክፉ
2. ከሰዎች (አእት መጽሐፍ ቅዱስ [ገጽ 867፣ ቁ. 32] "ከሚገድሉ ከእነርሱ፣" በሚል ያሻሽለዋል ማለትም፣ "ነፍሰ ገዳዮች" በሁለቱም ስንኞች በሀ እና ለ)
   ሀ. ዕድል ፈንታቸው ከዚህ ዓለም ከሆነ
   ለ. ሆዳቸው ከጠገበ
   ሐ. ብዙ ልጆች ካላቸው
   መ. ሀብታቸውን ለልጆቻቸው ለሚተዉ

ሆኖም፣ የመዝሙረኛው ባሕርይ
1. የእግዚአብሔርን ፊት በጽድቅ የሚሻ (የቅርበት ፈሊጥ፣ መዝ. 11፡7)
2. በእግዚአብሔር መገኘት የሚጠግብ (መዝ. 16፡11)

ሁለቱም ግሦች፣ የመዝ. 17፡15 ኀብራዊ ናቸው።
1. መመልከት/ማየት — ቢዲቢ 302፣ ኬቢ 301፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በኅብራዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. የረካ — ቢዲቢ 959፣ ኬቢ 1302፣ ቃል ኅብራዊ

**17፡15** ኃጢአተኛ (እና ዝርያዎቻቸው) ይረካሉ (ቢዲቢ 959፣ ኬቢ 1302፣ ቃል ያልተጠናቀቀ) በሥጋዊ ነገሮች፣ በክፋት በሚገኙ ጠቀሜታዎች፤ ዘማሪው (ለ "እኔ" አጽንዖት ይሰጣል)፣ በያህዌ መገኘት ስለ መጥገቡ!

◘ **"ስነቃ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 884፣ ኬቢ 1098፣ ሂፊል ያልተወሰነ አወቃቀር) በብዙ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል።
1. ከእግዚአብሔር የተለየ ራዕይ መንቃት
2. ከሌሊት እንቅልፍ መንቃት
3. ከስካር መንቃት
4. ከሞት መንቃት

እንደሚመስለኝ ቁ. 4 ዐውደ-ጽሑፉን ይገጥማል (ማለትም፣ የያህዌ መገኘት፣ 2 ነገ. 4:31፤ ኢዮብ 14:12፤ መዝ. 23:24-25፤ 139:18፤ ኢሳ. 26:19፤ ኤር. 51:39፣57፤ ዳን. 12:2)። እንደዚያ ከሆነ፣ እንግዲያውስ የመዝሙር 16 እና የመዝሙር 17 መጨረሻ ተመሳሳይ ነው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ያህዌ የመዝሙረኛውን ንጹሕ ነኝ ማለት እንዴት ይመለከተዋል?
2. መዝሙረኛው እንዴት ንጹሕ ነኝ ይላል?
3. "በቀኝህ" የሚለውን ምናባዊ ምስያ አብራራ።
4. "የዓይን ብሌን" የሚለውን ምናባዊ ምስያ አብራራ።
5. "በክንፎችህ ጥላ ሥር" የሚለውን ምናባዊ ምስያ አብራራ።

# መዝሙር 18
## የአዲሶቹ ትርጕሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ ማዳንን በማድረጉ ይመሰገናል<br><br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>"ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር፣ የጌታ አገልጋይ፣ የዚህን የመዝሙር ቃል ለጌታ የተናገረ፣ ጌታ ከጠላቶቹ ሁሉና ከሳኦል እጅ ባዳነው ጊዜ። አለም…፣ 18:1-3 | አምላክ ሉዓላዊው አዳኝ | ንጉሥ ምስጋና ያቀርባል፣ በጦርነት ድል በማድረጉ (ንጉሣዊ ምስጋና፣ 2 ሳሙ. 22፡ 1-3) | የዳዊት የድል መዝሙር | የንጉሥ ምስጋና |
| | 18:1-3 | 18:1-3 | 18:1 | 18:1 |
| | | | 18:2-3 | 18:2 |
| 18:4-6 | | | | |
| | | | | 18:3 |
| | 18:4-6 | 18:4-5 | 18:4-6 | 18:4-5 |
| 18:7-15 | | | | |
| | | 18:6 | | 18:6 |
| | 18:7-12 | 18:7-15 | 18:7-15 | 18:7-8 |
| | | | | 18:9-10 |
| | | | | 18:11-12 |
| | 18:13-15 | | | 18:13-14 |
| 18:16-19 | | | | |
| | | 18:16-19 | 18:16-19 | 18:15 |
| | 18:16-19 | | | 18:16-17 |
| 18:20-24 | | | | |
| | | 18:20-24 | 18:20-24 | 19:18-19 |
| | 18:20-24 | | | 18:20-21 |
| | | | | 18:22-23 |
| 18:25-29 | | | | |
| | | 18:25-30 | 18:25-27 | 18:24-25 |
| | 18:25-27 | | | |
| | | | 18:28-29 | 18:26-27 |
| 18:30-36 | | | | |
| | 18:28-30 | | 18:30-34 | 18:28-29 |
| | | 18:31-42 | | |
| | | | | 18:30 |
| | 18:31-34 | | | 18:31-32 |
| | | | 18:35-42 | |
| | | | | 18:33-34 |
| 18:37-42 | | | | |
| | 18:35-36 | | | 18:35-36 |
| | 18:37-42 | | | 18:37-38 |
| | | | | 18:39-40 |
| | | 18:43-45 | | |
| 18:43-45 | | | 18:43-45 | |
| | | | | 18:41-42 |
| | 18:43-45 | | | |
| | | | | 18:43 |
| | | 18:46-48 | | |
| 18:46-50 | | | 18:46-50 | |
| | | | | 18:44-45 |
| | 18:46-49 | | | |
| | | | | 18:46-47 |
| | | 18:49-50 | | |
| | | | | 18:48 |
| | | | | 18:49 |
| | 18:50 | | | |
| | | | | 18:50 |

## የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

# የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 18፡1-3**

**[1]እቤቱ ጒልበቴ ሆይ፥ እወድድሃለሁ።**
**[2]እግዚአብሔር ዓለቴ፥ አምባዬ፥ መድኃኒቴ፥**
**አምላኬ፥ በእርሱም የምተማመንበት ረዳቴ፥**
**መታመኛዬና የደኅንነቴ ቀንድ መጠጊያዬም ነው።**
**[3]ምስጋና የሚገባውን እግዚአብሔርን እጠራለሁ፥**
**ከጠላቶቼም እድናለሁ።**

**18፡1-3** መዝሙረኛው አምላኩን ያመለክታል፣ ተለጣጣቂ በሆኑ ብርቱ መጠሪያዎች እና ጠቃሾች (2 ሳሙኤል 22 ላይ ካለው ተመሳሳይ የሆነ ግጥም)። በሕይወት ውጥረቶች መካከል የፍጥረታትን አምላክና ተቤዢን የማይለወጥ ባሕርይ ያውቃል። በ"እኔ" ተውላጠ ስሞች ላይ ያሉትን የግል ነገሮች ተገንዘብ።

1. የእኔ ብርታት – ቢዲቢ 305፣ ኬቢ 304፣ ስም እዚህጋ ብቻ እና 1 ሳሙ. 22:2 ላይ
2. ዓለቴ (ሁለቴ) – ሁለት የተለያዩ የዕብራይስጥ ሥሮች
   ሀ. ቢዲቢ 700 I – መዝ. 31:3፤ 42:10፤ 71:3
   ለ. ቢዲቢ 849 – ዘዳ. 32:4፣15፣30
3. ምሽጌ – ቢዲቢ 845 II፣ ኬቢ 622፣ መዝ. 31:3፤ 71:3፤ 91:2፤ 144:2
4. አዳኜ – ቢዲቢ 812፣ ኬቢ 930፣ ፔል አንቀጽ። መዝ. 40:17፤ 70:5፤ 144:2
5. አምላኬ (ኤል) በእርሱም የምታመንበት – ቢዲቢ 340፣ ኬቢ 337፣ ቃል ያልተጠናቀቀ መዝ. 2:12፤ 5:11፤ 7:1፤ 11:1፤ 16:1፤ 25:20፤ 31:1፤ 37:40፤ 57:1፤ 61:5፤ 64:10፤ 71:1፤ 118:8-9፤ 141:8፤ 143:9፤ 144:2፤ ምሳ. 30:5
6. ጋሻዬ – ቢዲቢ 171፣ ኬቢ 545 I፣ መዝ. 3:3፤ 7:10፤ 18:30፣35፤ 28:7፤ 33:20፤ 59:11፤ 84:11፤ 115:9-11፤ 119:114፤ 144:2፤ ምሳ. 2:7፤ 30:5
7. የደኅንነቴ ቀንድ
   ሀ. "ቀንድ" (ቢዲቢ 901) – የኃይል ወይም የጥንካሬ ፈሊጥ መዝ. 75:10
   ለ. "ቀንድ" "ኮረብታ" ማለት ሊሆን ይችላል። ኢሳ. 5:1፤ እንደዚያ ከሆነ፣ እሱ ተመሳሳይ ምናባዊ ምስያ ነው፣ ለምሽግ ወይም ለመሸሸጊያ (ኒዶቴ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 991)
8. መሸሸጊያዬ – ቢዲቢ 960 I፣ ኬቢ 640፣ መዝ. 9:9፤ 46:7፣11፤ 48:3፤ 59:9፣16፣17፤ 62:2፣6፤ 94:22፤ 144:2
9. መመስገን የሚገባው እግዚአብሔር – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ፑኣል አንቀጽ፣ መዝ. 48:1፤ 96:4፤ 145:3

የእነዚህ ቃላት ክምችት፣ ደኅንነት፣ ጥበቃ፣ እና አስተማማኝነት ኃይለኛና በስሜት የተሞላ ነው። ሕይወት በወደቀው ዓለም አስቸጋሪ፣ ኢ-ፍትሐዊ፣ እና ሊታሰብ የማይችል ነው፣ ግን ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር አለ፣ እሱም የዚያ ሁነኛ ተቃራኒ የሆነ!

**18:1 "ፍቅር"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 933፣ ኬቢ 1216፣ ቃል ያልተጠናቀቀ) ተመሳሳይ የዕብራይስጥ ሥር ነው (□חר) እንደ "ማኅፀን"፣ ነገር ግን ይህንን ብዙ ከማንበባችን በፊት፣ ተመሳሳዩ ሥር "ጆፈ አሞራ" ማለት ነው! ሥርወ-ቃልን ተጠንቀቁ፣ የፍቺ ብቸኛው ምንጭ አለመሆኑን። ዐውደ-ጽሑፍ ፍችን ይወስነዋል!

የዚህ ግሥ የቃል ግንድ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ እሱም ሰው ለእግዚአብሔር ያለውን ፍቅር ያመለክታል። የፔይል ግንድ እጅግ በተሻለ የተለመደ ነው፣ እናም እሱ የእግዚአብሔርን ርኅራኄ ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ለሰው ልጅ ኪዳን ያለውን (ዘጸ. 33:19፤ ዘዳ. 13:13፤ 30:3፤ ኢሳ. 14:1፤ 27:11፤ 30:18፤ 49:10፣13፤ 54:8፣10፤ 55:7፤ 60:10)።

ይህ ግሥ ከ2 ሳሙኤል 22 ጋር ትይዩ አልተደረገም እናም ቢዲቢ የሚያስበው የተጨመረ ሳይሆን እንደማይቀር ነው፣ ሊሆን የሚችለውም መዝሙሩ ለማኅበረሰቡ የአምልኮ መገልገያ ሲሆን።

**መዝሙር ፡ 18:4-6**

***4የሞት ጣር ያዘኝ፥***
***የዓመፅ ፈሳሽም አስፈራኝ***
***5የሲኦል ጣር ከበበኝ***
***የሞት ወጥመድም ደረሰብኝ።***
***6በጨነቀኝ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት፥***
***ወደ አምላኬም ጮኽሁ***
***ከመቅደሱም ቃሌን ሰማኝ፥***
***ጩኸቴም በፊቱ ወደ ጆሮው ገባ።***

**18:4-5** መዝሙረኛው መከራውን ይገልጻል፣ ግልጽ በሆነ፣ ትይዩአዊ፣ ቅኔአዊ ቋንቋ።

1. ጣር (ማለትም፣ ወጥመድ፣ ምሳ. 13:14፤ 14:27) የሞት ያዘኝ — ቢዲቢ 67፣ ኬቢ 79፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 116: 3፤ ሊሆን የሚችለው "ጣር" 2 ሳሙኤል 22ን ተከትሎ፣ እንደ "ማዕበል" ነው መረዳት የሚቻለው፣ እሱም ከቀጣዩ የቅኔ ሐረግ ጋር መልካም ትይዩነትን የሚፈጥር። ኒዶቴ ቅጽ 1 ገጽ 482፣ የሚጠቅሰው ዲኤስኤስ (አይኪውኤች 3:28፤ 5: 39) ግሡን እግዚአብሔርን ለማመስገን ይጠቀምበታል፣ ስለ ማዳኑ ከ
   ሀ. "ሞት ጣር"
   ለ. "ከጥፋት ወንዞች"
   ይህም ደግሞ ከዐውደ-ጽሑፉ ጋር እዚህ ይገጥማል።
2. የቢልኣል ማዕበል (ቢዲቢ 116፣ ናሆ. 1:15፤ 2 ቆሮ. 6:15) አስፈራኝ – ቢዲቢ 129፣ ኬቢ 147፣ ፒይል ያልተጠናቀቀ፤ ግሡ ዘወትር ኢዮብጋ ጥቅም ላይ ይውላል (ኢዮብ 3:5፤ 9:34፤ 13:11፣21፤ 15:24፤ 18:11፤ 33:7)። 2 ሳሙ. 22:5 "ቢሊአል" "ጥፋት" በሚል ነው የተተረጎመው፣ እሱም ሰዋዊ አለመሆኑን ሊያመለክት የሚችል
3. የሲኦል ጣር (መዝ. 1:6 ላይ ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት) ከበበኝ – ቢዲቢ 685፣ ኬቢ 738፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 17:11፤ 22:12፣16፤ 49:5፤ 88:17፤ 118:10-12
4. የሞት ወጥመድም ደረሰብኝ — ቢዲቢ 869፣ ኬቢ 1068፣ ፔይል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 18:18፤ ኢዮብ 30:27

"የእኔ" መዝ. 18:1-3 ላይ የተተኮረበት እንደሆነ፣ አሁን ደግሞ "እኔ" ለጥቃት እንደተጋለጠ ቁጥር 4-5 ላይ ተተኩሮበታል። እያንዳንዱ ሰው ሞትን ይፈራል፣ ከሕይወት አምላክ ጋር የተያያዘ ግላዊ እምነት እስከሌለው ድረስ (1 ዮሐንስ 4:7-21)! ሰይጣን ሞትን አይቆጣጠርም፣ ነገር ግን የሞት ፍርሃትን ያጋንናል።

**18:6** ቁጥር 6 የመዝሙረኛው ምላሽ ነው፣ እየቀረበበት ላለው የሞት ስሜት (ማለትም፣ "መከራ" ቢዲቢ 856 II፣ ኢዮብ 15:24፤ 38:23፤ መዝ. 66:14፤ 119:143)።

1. ጌታን ጠራሁት – ቢዲቢ 894፣ ኬቢ 1128፣ ቃል ያልተጠናቀቀ
2. ወደ እግዚአብሔር ጮኽኩ – ቢዲቢ 1002፣ ኬቢ 1443፣ ፒይል ያልተጠናቀቀ

ጸሎቱ ተመልሷል።

1. ከመቅደሱ ሆኖ ድምጼን ሰማ
2. ጩኸቴን ለዕርዳታ ሰማ፣ ገና ጆሮው ሳይደርስ (መዝ. 6:8-9፤ 28:2፣6)

የስንኝ 1 እና 2ን ትይዩነት ተገንዘብ፣ ከዚያም የስንኝ 3 እና 4። ይህ ተመሳሳይ ትይዩነት የዕብራይስጥ ቅኔ ባሕርይ ነው (የመግቢያውን ጽሑፍ ተመልከት)። የጥበቃ አምላክ ደግሞ ለጸሎት ምላሽ የሚሰጥም አምላክ ነው!

**መዝሙር ፡ 18:7-15**

***7ምድርም ተንቀጠቀጠች ተናወጠችም፥***
***የተራሮችም መሠረቶች ተነቃነቁ፥***
***እግዚአብሔርም ተቈጥቶአልና ተንቀጠቀጡ።***
***8ከቍጣው ጢስ ወጣ፥***

ከፊቱም የሚበላ እሳት ነደደ
ፍምም ከእርሱ በራ።
9ሰማዮችን ዝቅ ዝቅ አደረገ ወረደም፥
ጨለማ ከእግሩ በታች ነበረ።
10በኪሩቤልም ላይ ተቀምጦ በረረ፥
በነፋስም ክንፍ በረረ።
11መሰወሪያውን ጨለማ አደረገ በዙሪያውም ድንኳኑ
በደመናት ውስጥ የጨለማ ውኃ ነበረ።
12በፊቱ ካለው ብርሃን የተነሣ ደመናትና
በረዶ የእሳት ፍምም አለፉ።
13እግዚአብሔርም ከሰማያት አንጐደጐደ፥
ልዑልም ቃሉን ሰጠ።
14ፍላጻውን ላከ በተናቸውም
መብረቆችን አበዛ አወካቸውም።
15አቤቱ፥ ከዘለፋህ ከመዓትህም
መንፈስ እስትንፋስ የተነሣ፥
የውኆች ምንጮች ታዩ፥
የዓለም መሠረቶችም ተገለጡ።

**18፡7-15** ይህ አንጓ እግዚአብሔር ለመዝሙረኛው ጸሎት የሰጠውን ምላሽ ይገልጻል። እግዚአብሔር ለድርጊት ተነሥቷል (ማለትም፣ [1] የቅዱስ ጦርነት ምናባዊ ምስያ ወይም [2] ከዙፋኑ ተነሥቷል)!

1. ቁጥር 7 ላይ የታማኝ ተከታይ መከራ ለመለኮታዊ ቁጣ ምክንያት ይሆናል (ቢዲቢ 354፤ ኬቢ 351፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 2፡4-6 ላይ)። ይህ የሚነድ ቁጣ (የምድር መንቀጥቀጥን ምስያ ያደረገኘ ኢሳ. 29፡6) ቁጥር 8 ላይ ባሕርዩ ተገልጧል (ማለትም፣ ነጎድጓድ፣ ምናባዊ፣ ዘዳ. 33፡26፤ ኢሳ. 29፡6)። እሱም ሊባል የሚችለው ይህ ምናባዊ ዘጸ. 19፡18-19ን እንደሚያንጸባርቅ ነው (ማለትም፣ የሙሴ ኪዳን በሲና ተራራ መሰጠቱ)።
2. የያህዌ ምላሽ ባሕርይ ያደረገው በነጎድጓድ ድምጽ ምስያ ነው፣ ቁጥር 9-15 ላይ።
   ሀ. ሰማያትን ዝቅ አደረገ (ኢሳ. 64፡1)። የተእመቅ (የተከለሰው እንግሊዝኛ መጽሐፍ ቅዱስ) ሐረጉን ዳግም ያበጀዋል እናም፣ “እሱ ሰማያትን ከፈለ” የሚል አለው። ይኸው ተመሳሳይ ምስያ ኢሳ. 34:4፤ ራዕ. 6:12-14 ላይ ተንጸባርቋል።
   ለ. በጥቅጥቅ ጨለማ ወረደ
   ሐ. ጨለማ በውኃዎች ላይ
   መ. ጥቅጥቅ ደመናት በሰማያት
   ሠ. በፊቱም ብሩኅ ብርሃን
   ረ. ድኝ እና እቶን እሳት
   ሰ. የሰማያት ላይ ነጎድጓድ
   ሸ. የሚያበራ መብረቅ
   ቀ. የውኃ ፈሳሽ

በብዙ መንገዶች ይህ ገለጻ የሚጠቅሰው *ሼከናህ* የክብር ደመናን ነው፣ በምድረ-በዳ የመንከራተት ጊዜ፣ ሁለቱንም፣ ያህዌን ለመከለልና ለመግለጥ (ዘጸ. 13:21-22፤ 19:19-20፣24፤ 16:10፤ 19:9፣16፤ 24:15-18፤ 40:34-38)።

**18፡7 “ምድር ተንቀጠቀጠች ተናወጠችም”** ትርጓሜያዊ ጥያቄ የሚሆነው፣ “ይህ በጥሬው ነው ወይስ ዘይቤአዊ?”

1. የጥሬ — የእነርሱ የምድር መንቀጥቀጥ ምስያ፣ የእግዚአብሔር መምጣትና መገኘት ነው፣ ዘጸ. 19:18፤ መዝ. 68:7-8
2. ዘይቤአዊ — “የምድር” ሰውኛ ዘይቤ መሆን
   ሀ. ምድርም አወጣች– ዘፍ. 1:12፣24
   ለ. ምድር ዋጠቻቸው – ዘጸ. 15:12፤ Num. 16:34
   ሐ. ምድር ተፋች – ሌዋ. 18:25፣28፤ 20:22
   መ. ምድር አፏን ከፈተች – ዘኍ. 16:32፤ 26:10፤ ዘዳ. 11:6፤ መዝ. 106:17
   ሠ. ምድር እንደ ምስክር – ዘዳ. 4:26፤ 30:19፤ 31:28፤ 32:1
   ረ. ለምድር ተናገር – ኢዮብ 12:8፤ 16:18፤ መዝ. 50:4
   ሰ. ምድር ትነሣባቸዋለች – ኢዮብ 20:27
   ሸ. ምድር ጮኸች – ኢዮብ 31:38
   ቀ. ምድር ያህዌን ታመሰግናለች – መዝ. 69:34
   በ. ምድር ትደሰታለች – መዝ. 96:11፤ 97:1
   ተ. ምድር ተንቀጠቀጠች – መሳ. 5:4፤ 1 ሳሙ.14:15፤ ኢሳ. 13:13

ቸ. ምድር አዘነች – ኢሳ. 24፡4፤ 33፡9፤ ሆሴ. 4፡3

**18፡8 "እሳት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 11፡6 ላይ።

**18፡9 "እሱ... ወረደ"** ያህዌ የሚኖረው በሰማይ ነው። የእርሱ መገኛ መኖርያው በኪዳኑ ታቦት ላይ በኪሩቤል መካከል ነው፣ ነገር ግን ከጊዜ ወደ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ሰዎች ስለ መምጣቱ የሚለው በተለያዩ መንገዶች ነው (ማለትም፣ ቲዎፋኒስ፣ ዘጸአት 3)። ዘጸአት 3፡7-8 ያህዌ ለሕዝቡ ስለሰጠው ምላሽ የተለየ ምሳሌ ነው፣ በእነርሱ በኩል ሆኖ ለፍላጎታቸው መሥራቱ። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ምስያው የሚገለጸው በበጽኑ የነጎድጓድ ወጀብ ነው።

**18፡10-11** ይህም ያህዌን ይገልጻል በነጎድጓድ ድምጽ ምስያ። ዝናብ ለከፊል በረሀማ ነዋሪዎች ጠቃሚ ነው፣ ወጀብ ግን አስፈሪ ነው። በእስራኤል ታሪክ ወደ ከነአን ከገቡ በኋላ እስራኤላውያን በመራባት ጣዖት በተለይም በበአል፣ በወጀብ ጣዖት፣ ዝናብና ምርትን የሚሰጥ ተጽዕኖ ሥር ወድቀው ነበር። ሆኖም፣ እውነተኛው "የወጀቡ አምላክ" ያህዌ ነበር (የዘጸአት 19ን ምስያ ተገንዘብ)።

**18፡10 "ኪሩብ"** ትይዩአዊውን ምስያ መዝ. 104፡3 ላይ ተመልከት። ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ ኪሩቤል

ሀ. ከብዙዎቹ መልአካዊ ሕላዌዎች አንዱ ነው። ይህ የተለየ ዓይነት ቅዱስ ቦታዎችን ይጠብቃል (ዘጸ. 25፡18-22፤ 1 ነገሥ. 8፡6-7)።

ለ. ሥርወ ቃሉ ርግጠኛ አይደለም፡

1. ከአካድያን "ጣልቃ የሚገባ" ወይም "አማላጅ" በእግዚአብሔርና በሰው መሐል
2. ከዕብራይስጥ ይህ የቃላት አግባብ ነው፣ "ሠረገላ" እና ኪሩብ" (ሕዝ. 1፤10)
3. አንዳንዶች የሚሉት፣ እሱ የሚለው "ብሩኅ ገጽታ" ነው

ሐ. አካላዊ ቅርጹ— ይህን ለማረጋገጥ ያስቸግራል፤ ምክንያቱም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ባለ የተለያየ ገለጻ እና የተለያየ እንስሳ-ሰው
ቅርጽ፣ በጥንታዊ የቅርብ ምስራቅ በሚገኙት። አንዳንዶች የሚያያይዟቸው

1. ከክንፋማ የሞሶፖታሚያ በሬዎች
2. ክንፋማ የግብፅ የአሞራ-አንበሶች፣ "ግሪፊንስ" ተብለው የሚጠሩት
3. የሂራም ክንፋማ ፍጥረታት፣ የጢሮስ ንጉሥ ዙፋን
4. የግብፅ ስፊኒክስ እና በንጉሥ አሃብ የዝኖን ጥርስ ሜተ መንግሥት በሰማሪያ የሚገኙት ተመሳሳይ ዓይነቶች

መ. አካላዊ ገጽታ

1. ኪሩቤል የሚለው ቅርጽ የሚያያዘው ከኢሳይያስ 6 ሱራፌል ጋር ነው
2. የተለያዩ ቅርጾች ምሳሌዎች
   - ሀ. የፊታቸው ቁጥር
     1) ሁለት- ሕዝ. 41፡18
     2) አራት- ሕዝ. 1፡6፣ 10፤ 10፡14፣16፣21፣22
     3) አንድ- ራዕ. 4፡7
   - ለ. የክንፎች ቁጥር
     1) ሁለት- 1ኛ ነገሥ. 6፡24
     2) አራት- ሕዝ. 1፡6፣11፤ 2፡23፤ 10፡7፣8-21
     3) ስድስት (እንደ ኢሳ. 6፡2 ሱራፌልን የመሰለ)- ራዕ. 4፡8
3. ሌሎች ገጽታዎች
   - ሀ. የሰው እጆች- ሕዝ. 1፡8፤ 10፡8፣21
   - ለ. እግሮች
     1) ቀጥ ያለ፣ ጉልበት የሌለው- ሕዝ. 1፡7
     2) የጥጃ እግር- ሕዝ. 1፡7
3. ፍላቪየስ ጆሴፈስ ማንም ኪሩቤል ምን እንደሚመስሉ የሚያውቅ እንደሌለ ተቀብሏል *(የአይሁድ **አንቲኩቲ**ስ፣* VIII፡3፡3)።

ሠ. በመጽሐፍ ቅዱስ የተገኙ ቦታዎችና ተግባራት

1. የሕይወት ዛፍ ጠባቂዎች፣ ዘፍ. 3፡24 (ምናልባትም ለሰይጣን በዘይቤነት ጥቅም ላይ ውለዋል በሕዝ. 28፡14፣16)
2. የመቅደሱ ጠባቂዎች

ሀ. በኪዳኑ ታቦት ላይ፤ ዘጸ. 25፡18-20፤ ዘኁ. 7:89፤ 1 ሳሙ. 4:4
ለ. በመሸፈኛና አመጋረጃ የሚከለል፤ ዘጸ. 26፡1፣31፤ 36:8፣35

3. የሰሎሞን መቅደስ ጠባቂዎች
   ሀ. ሁለት ትላልቅ የሚያዣብቡ ኪሩቤል በቅድቅተ ቅዱሳን፤ 1 ነገሥ. 6:23-28፤ 8:6-7፤ II ዜና. 3:10-14፤ 5:7-9
   ለ. በውስጠኛው ሽሪን ግድግዳ ላይ፤ 1ኛ ነገሥ. 6:29,35፤ II ዜና. 3:7
   ሐ. ከብዙ ላቬርስ ጋር በሚገናኙ ከፈፎች ጋር፤ 1ኛ ነገሥ. 7:27-39
4. የሕዝቅኤል መቅደስ ጠባቂዎች
   ሀ. በግድግዳና በበር ላይ የተለበጡ፤ ሕዝ.41፡18-20፣ 25
5. ከመለኮት መጓጓዣ ጋር የተያያዙ
   ሀ. የንፋስ ዘይቤ ሊሆን የሚችል፤ 2ኛ ሳሙ. 22፡11፤ መዝ. 18፡10፤ 104:3-4፤ ኢሳ. 19፡1
   ለ. የእግዚአብሔር ዙፋን ጠባቂዎች፤ መዝ. 80፡1፤ 99፡1፤ ኢሳ. 37፡16
   ሐ. የእግዚአብሔር ተንቀሳቃሽ ዙፋን ሠረገላ ጠባቂዎች፤ ሕዝ. 1፡4-28፤ 10:3-22፤ 1 ዜና. 28፡18
6. የሔሮድስ መቅደስ
   ሀ. በግድግዳዎች ላይ ተስሏል (ማለትም፣ የታልሙድ "ዮማ" ጠባቂ 54ሀ)
7. የራዕይ የዙፋን ትዕይንት (ማለትም፣ ጠባቂ ራዕ. 4-5)

**18፡11 *"መሰወሪያውን ጨለማ አደረገ"*** በብኪ ያህዌን ማየት ማለት ሞት ነው (ዘፍ. 16፡13፤ 32:30፤ ዘጸ. 3:6፤ 33:20፤ መሳ. 6:22-23፤ 13:22፤ 1 ነገ. 19፡13፤ ኢሳ. 6:5፤ ሐዋ. 7:32)። ጥቅጥቁ ጥቁር ደመና እስራኤላውያንን የመከላከያ መንገድ ነበር (ዘጸ. 19:9፤ 20:21፤ ዘዳ. 4፡11፤ 5:23)።

**18፡15 "የምድር *መሠረቶች*"** ይህ ምስያ የሚገለጸው እንደ
1. የምድር ምሰሶዎች – 1 ሳሙ. 2:8፤ ኢዮብ 9:6፤ 38:4-6፤ መዝ. 75:3፤ 104:5
2. የተራሮች መሠረቶች – ዘዳ. 32:22፤ ኢዮብ 28:9፤ ዮናስ 2:6

ሊሆን የሚችለው፣ ቁጥር 15 የያህዌን ታላቅ የማዳን ሥራ የሚጠቅስ ነው
ሀ. በስድ ንባብ – ዘጸ. 14፡21-22፣29
ለ. በቅኔ – ዘጸ. 15:8፤ መዝ. 106:9

***መዝሙር* ፡ 18፡16-19**

**16ከላይ ሰደደ ወሰደኝም፥**
**ከብዙ ውኆችም አወጣኝ።**
**17ከብርቱዎች ጠላቶቼ**
**ከሚጠሉኝም አዳነኝ፥ በርትተውብኝ ነበርና።**
**18በመከራዬ ቀን ደረሱብኝ**
**እግዚአብሔር ግን ደገፋዬ ሆነ።**
**19ወደ ሰፊ ስፍራም አወጣኝ**
**ወድዶኛልና አዳነኝ።**

**18፡16-19** ይህ አንጓ የሚገልጸው ያህዌ መዝሙረኛውን እንዳዳነ ነው። ደግሞም ቁጥር 6 ላይ ያለው "መከራ" አሁን ግልጽ የሆነው እንደ "የሚጠሉኝ፣ ከእኔ እጅግ ብርቱዎች ናቸው። በመከራዬ ቀን ተነሡብኝ" (መዝ. 59፡16-17)!
1. ከላይ ላከ፣ ወሰደኝም፣ መዝ. 144፡7
2. ከብዙ ውኆች አወጣኝ፣ መዝ. 32፡6
3. ከብርቱ ጠላቴ አዳነኝ
4. ከሚጠሉኝ አዳነኝ
5. ወደ ሰፊ ስፍራ አወጣኝ፣ የነጻነት ፈሊጥ፣ መዝ. 4፡1፤ 31:8፤ 118:5
6. አዳነኝ፣ በእኔ ላይ ፊቱን ስላበራ፣ ዝከ. 2 ሳሙ. 22:20፤ መዝ. 37:23፤ 41፡11፤ 147፡11

**18፡16 "ከብዙ ውኆችም አወጣኝ"** ይህ ሥር፣ מ–ה (ቢዲቢ 602፣ ኬቢ 642) የሚገኘው (1) እዚህ ብቻ [እና በትይዩ 2 ሳሙ. 22፡17 ላይ ነው] እና (2) በሙሴ የመዳን ጉዳይ ዘጸ. 2፡10 ላይ። እሱም ታዋቂ ሥርወ-ቃል ሆኗል፣ "ሙሴ" ለሚለው ስም።
"ብዙ ውኆች" በሁለት መንገድ መረዳት ይቻላል።
1. ዐውደ-ጽሑፋዊው ዘይቤ፣ ቀውጢ/ችግሮች/ጥቃቶች (መዝ. 32:6፤ 46፡1-3፤ 69፡1-2፤ 124፡1-5፤ 144:5-8፤ ኢሳ. 43:2

2. በዘፍጥረት የያህዌ ጉዳይ ጠቃሽ፣ የውኃዎችን ነውጦች ማሸነፉ (መዝ. 74፡13-14፤ 89፡9-10፤ 104፡6-7፤ ኢሳ. 51፡9-10፣ የጀሮምን የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ ተመልከት ገጽ 578፣ እና የእኔን ማስታወሻ፣ ዘፍጥረት 1፡2 ላይ "ጥልቁ" www.freebiblecommentary.org ላይ፣ ዘፍጥረት 1-11)

**መዝሙር ፡ 18፡20-24**

**[20]እግዚአብሔር እንደ ጽድቄ ይከፍለኛል**
**እንደ እጄ ንጽሕና ይመልስልኛል።**
**[21]የእግዚአብሔርን መንገድ ጠብቄአለሁና፥**
**በአምላኬም አላመፅሁም።**
**[22]ፍርዱ ሁሉ በፊቴ ነበረና፥**
**ሥርዓቱንም ከፊቴ አላራቅሁም።**
**[23]በእርሱ ዘንድ ቅን ነበርሁ፥**
**ከኃጢአቴም ተጠበቅሁ።**
**[24]እግዚአብሔርም እንደ ጽድቄ**
**እንደ እጄም ንጽሕና በዓይኖቹ ፊት መለሰልኝ።**

**18፡20-24** የቁ. 20ን አካታችነት ከቁ. 24 ጋር አወዳድረህ ተመልከት። ይህ አንጓ፣ ዘማሪው ኃጢአት የለሽነቱን ወይም ፍጽምናውን እንደሚገልጽ ተደርጎ መወሰድ አይኖርበትም። ከሥነ-መለኮት አኳያ እሱ "ያለ ነውር" መሆኑን አስረግጧል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ ከታች ያለውን)።

የእያንዳንዱን ጥንድ ትይዩነት ተመልከት።

1. እንደ ጽድቄ
2. እንደ እጆቼ ንጽሕና
3. የጌታን መንገድ ጠብቄአለሁ
4. ከእግዚአብሔር በክፋት አልራቅኩም
5. ሕግጋቱ ሁሉ በፊቴ ናቸው (ለቁ. 5 እና ቁ. 6 ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡2 ላይ)
6. የእርሱን ሕግ ከእኔ አላራቅኩም
7. በፊቱ ያለ-ነውር ነበርኩ
8. ራሴን ከበደሌ ጠብቄአለሁ

## ልዩ ርዕስ፡ ነውር የሌለው፣ ንጹሕ፣ ኃጢአት የሌለበት፣ ያለ ነውር

ሀ. የመክፈቻ መግለጫ

1. ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ከሥነ-መለኮት አኳያ የሚገልጸው የሰው ልጅን የመጀመሪያ አቋም ነው (ማለትም፣ ዘፍጥረት 1፣ የዔድን ገነት)።
2. ኃጢአትና ዐመፃ ይሄንን የፍጹም ኅብረት ሁኔታ ደምስሶታል (ማለትም፣ ዘፍጥረት 3)።
3. ሰዎች (ወንድና ሴት) ከእግዚአብሔር ጋር የነበራቸው ኅብረት እንዲመለስ ይናፍቃሉ፣ ምክንያቱም በእሱ መልክና አምሳል ስለተፈጠሩ ነው (ማለትም፣ ዘፍ. 1፡26-27)።
4. እግዚአብሔር ከኃጢአተኛ የሰው ልጅ ጋር በብዙ መንገድ ይሠራል
   ሀ. መልካም መሪዎች (ማለትም፣ አብርሃም፣ ሙሴ፣ ኢሳይያስ)
   ለ. መሥዋዕታዊ ሥርዓት (ማለትም፣ ሌዋውያን 1-7)
   ሐ. የመልካም ምሳሌዎች (ማለትም፣ ኖኅ፣ ኢዮብ)
5. በመዳረሻውም እግዚአብሔር መሲሕን ሰጠ
   ሀ. እንደ ራሱ ሙሉ መገለጫ
   ለ. ለኃጢአት የሚሆን ፍጹም መሥዋዕት
6. ክርስቲያኖች ኃጢአት የሌለባቸው ሆነዋል
   ሀ. በሕጋዊ መንገድ በክርስቶስ በተደረገ ጽድቅ በኩል
   ለ. መንፈስ ቅዱስ በቀጣይነት በሚሠራው ሥራ በኩል
   ሐ. የክርስትና ግብ ክርስቶስን መምሰል ነው (ሮሜ. 8፡28-29፤ ኤፌ. 1፡4)፣ እሱም በርግጥ፣ የእግዚአብሔር አምሳል የሆነውን ሰው መመለስ ነው፣ በአዳምና ሔዋን ውድቀት የጠፋውን
7. መንግሥተ ሰማያት በዔድን ገነት ያለው ፍጹም ኅብረት መመለስ ነው። መንግሥተ ሰማይ ከእግዚአብሔር መገኛ የምትመጣ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ነች (ራዕ. 21፡2) ለነጻችው ምድር (2ኛ ጴጥ. 3፡10)።
   መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረውም የሚጨርሰውም በተመሳሳይ ጭብጦች ነው።
   ሀ. የቅርብ ወዳጅነት፣ ግላዊ ኅብረት ከእግዚአብሔር ጋር
   ለ. በገነት ስፍራ (ዘፍጥረት 1-2 እና ራዕይ 21-22)
   ሐ. በትንቢታዊ መግለጫ፣ የእንስሳት መገኘትና ጓደኝነት (ኢሳ. 11፡6-9)።

ለ. ብሉይ ኪዳን

1. በርካታ የሚሆኑ የተለያዩ የዕብራይስጥ ቃላት አሉ፣ የፍጽምናን፣ ያለ ነውር መሆንን፣ የንጹሕነትን ጽንሰ-ሐሳብ የያዙ፣ እነሱም ለመሰየምና ውስብስብ የሆነውን ዝምድና ለማሳየት።
2. ዋነኞቹ ቃላት የፍጽምናን፣ ያለ ኃጢአት መሆንን፣ ወይም ንጽሕናን የያዙ ጽንሰ ሐሳቦች (እንደ ሮበርት ቢ ጊርድልስቶን፣ የብሉይ ኪዳን ተመሳስሎ፣ ገጽ 94-99)
   ሀ. ሻሎም (ቢ.ዲ.ቢ. 1022)
   ለ. ታማም (ቢ.ዲ.ቢ. 1070)
   ሐ. ካላህ (ቢ.ዲ.ቢ. 478)
3. ሴፕቱዋጂንት (ማለትም፣ የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ) እነዚህን በርካታ ጽንሰ-ሐሳቦች ወደ ኮኔ ግሪክ ቃላት ይተረጉሟቸዋል፣ በአኪ።
4. ቁልፉ ጽንሰ-ሐሳብ የተያያዘው ከመሥዋዕታዊ ሥርዓት ጋር ነው
   ሀ. *amōmos (አሞሞስ)* (ዘጸ. 29:1፤ ሌዋ. 1:3፣10፤ 3:1፣6፤ ዘኁ. 6:14)
   ለ. *amiantos (አሚያንቶስ) እና aspilus (አስፒለስ) ደግሞ* ወጣ ያለ ፍቺዎች አሉት

ሐ. አዲስ ኪዳን
1. ሕጋዊው ጽንሰ ሐሳብ
   ሀ. የዕብራይስጥ ሕጋዊ ጽንፈኛ ፍቺ የሚተረጎመው በአሞሞስ ነው (ኤፌ. 5:27፤ ፊሊጵ. 2:15፤ I ጴጥ. 1:19)
   ለ. የግሪክ ሕጋዊ ፍቺ (I ቆሮ. 1:8፤ ቆላ. 1:22)
2. ክርስቶስ ኃጢአት የሌለበት፣ ያለ ነውር፣ ንጹሕ የሆነ ብቸኛው ነው (አሞሞስ፣ ዕብ. 9:14፤ I ጴጥ. 1:19)
3. የክርስቶስ ተከታዮች እሱን መምሰል አለባቸው (አሞሞስ፣ ኤፌ. 1:4፤ 5:27፤ ፊሊጵ. 2:15፤ ቆላ. 1:22፤ II ጴጥ. 3:14፤ ይሁዳ ቁ. 24፤ ራዕ. 14:5)
4. ይህ ጽንሰ ሐሳብ ስለ ቤተ ክርስቲያን መሪዎች ጥቅም ላይ ይውላል
   ሀ. *anegklētos*፣ (አኔክሊቶስ) "ያለ ምንም ክስ" (1ኛ ጢሞ. 3:10፤ ቲቶ 1:6-7)
   ለ. *anepileptos*፣ (አኒፒሊፕቶስ) "ያለ ነቀፋ" ወይም "ነቀፌታ የሌለበት" (1ኛ ጢሞ. 3:2፤ 5:7፤ 6:14፤ ቲቶ 2:8)
5. "ያለ ነውር" የሚለው ጽንሰ ሐሳብ (*amiantos)* (አሚያንቶስ) ጥቅም ላይ የሚውለው
   ሀ. ክርስቶስ ራሱ (ዕብ. 7:26)
   ለ. የክርስቲያኖች ውርስ (1ኛ ጴጥ. 1:4)
6. የ "ጤነኝነት" ወይም "ደኅንነት" ጽንሰ ሐሳብ (*holoklēria ሆሎክሌሪያ* ሐዋ. 3:16፤ I ተሰ. 5:23፤ ያዕቆብ 1:4)
7. "ያለ ጥፋት፣" ኃጢአት የለሽ ንጽህና የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ የሚታወቀው አሚምቶስ ነው (ሉቃስ 1:6፤ ፊሊጵ. 2:15፤ 3:6፤ 1ኛ ተሰ. 2:10፤ 3:13፤ 5:23)
8. "ነውርን የማይከተል" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ የሚታወቀው በአሞምቶስ ነው (1ኛ ጴጥ. 3:14)
9. "ነውር የሌለው፣" "ያለ ነቀፋ" የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ከላይ ያሉት ቃላት ባሏቸው አንቀጾች ነው (1ኛ ጢሞ. 6:14፤ ያዕቆብ 1:27፤ I ጴጥ. 1:19፤ II ጴጥ. 3:14)

መ. በዕብራይስጥና በግሪክ ያሉት በዛ ያሉ ቃላት ይሄንን ጽንሰ ሐሳብ የሚገልጹ፣ ጠቀሜታውን ያሳያሉ። እግዚአብሔር የሚያስፈልገንን በክርስቶስ በኩል አሟልቶልናል፤ አሁን ደግሞ እሱን እንድንመስል እየጠራን ነው።

አማኞች በአቋማዊ፣ በሕጋዊ፣ "እውነተኛ" "ትክክለኛ" "ያለ ነውር" ተደርገው ይወሰዳሉ፣ በክርስቶስ ሥራ። አሁን አማኞች ስፍራቸውን ሊወርሱ ነው። "በብርሃን ተመላለሱ፣ እሱ በብርሃን እንዳለ" (1ኛ ዮሐንስ 1:7። ለመጠራታችሁ እንደሚገባ ተመላለሱ (ኤፌ. 4:1፣17፤ 5:2፣15)። ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መልክ መልሶታል። አሁን የቅርብ ወዳጅነት ይቻላል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የእሱን ባሕርይ የሚያንጸባርቅ ሕዝብ እንደሚፈልግ አስታውሱ፣ ልጁ እንዳደረገው ሁሉ። እኛ የተጠራነው ከቅድስና ላነሰ ጉዳይ አይደለም (ማቴ. 5:20፣ 48፤ ኤፌ. 1:4፤ I ጴጥ. 1:13-16)። የእግዚአብሔር ቅድስና ሕጋዊ ብቻ አይደለም፣ ድርጊታዊም ነው እንጂ!

**18:20 "እሱ ይከፍለኛል"** ይህ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 996፣ ኬቢ. 1427) ተደግሟል በአንጓው መዝጊያ ላይ (ዝከ. ቁ. 24)። አለማመን ውጤት አለው፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ይመስገን፣ ለታማኝ ተከታዮች ግን ጠቀሜታ አለ! እነዚህ በተከታዩ አንጓ በዝርዝር ተመልክተዋል (መዝ. 18:25-29)።

***መዝሙር ፡ 18:25-29***

***25ከቸር ሰው ጋር ቸር ሆነህ ትገኛለህ***
***ከቅን ሰው ጋር ቅን ሆነህ ትገኛለህ***
***26ከንጹሕ ጋር ንጹሕ ሆነህ ትገኛለህ***
***ከጠማማም ጋር ጠማማ ሆነህ ትገኛለህ።***
***27አንተ የተጠቃውን ሕዝብ ታድናለህና፥***
***የትዕቢተኞችን ዓይን ግን ታዋርዳለህ።***
***28አንተ መብራቴን ታበራለህና***
***እግዚአብሔር አምላኬ ጨለማዬን ያበራል።***
***29በአንተ ከጥፋት እድናለሁና***
***በአምላኬም ቅጥሩን እዘልላለሁ።***

**18፡25-29** እነዚህ አስደናቂ፣ መለኮታዊ ውጤቶች ናቸው የታመነ አማኝን የሚከተሉ።

1. "ከቸር ሰው ጋር (ቢዲቢ 339)፣ ቸር ሆነህ ትገኛለህ" (ቢዲቢ 338፣ ኬቢ 336፣ ሂዝፔል ያልተጠናቀቀ፤ ይህ ቁጥርና ትይዩው 2 ሳሙ. 22፡26 ላይ ያለው፣ በብኪ ብቸኛ ስፍራዎች ናቸው፣ የግሡ መልክ የዚህ ልዩ ኪዳን ስም፣ ሄስድ፣ የሚከሰትበት፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7 ላይ)። "ከ...ጋር" (עם) ቁ. 25-26ን እንደሚያስተዋውቅ ተገንዘብ፣ "ለ" (כי ) ቁ. 27-29ን ሲያስተዋውቅ።
2. "ከቅን ሰው ጋር (ቢዲቢ 1071፣ ዝኪ. ቁ. 23) ቅን ሆሀ ትገኛለህ" (ቢዲቢ 1070፣ ኬቢ 1752፣ ሂዝፔል ያልተጠናቀቀ)።
3. "ከንጹሕ ጋር (ቢዲቢ 140፣ ኬቢ 162፣ ኒፋል ቦዝ አንቀጽ፣ ኢሳ. 52፡11) ንጹሕ ሆነህ ትገኛለህ" (ቢዲቢ 140፣ ኬቢ 162፣ ሂዝፔል ያልተጠናቀቀ)። ተቃራኒውን ትይዩነት ተመልከት የቁ. 26 እና 27።
4. "ከጠማማ ጋር (ቢዲቢ 786 I) ጠማማ ሆነህ ትገኛለህ" (ቢዲቢ 836፣ ኬቢ 990፣ ሂዝፔል ያልተጠናቀቀ)። "ጠማማ" የቅን ተቃራኒ ነው፣ እሱም ቀና የሆነውን የሚያመለክት፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡5 ላይ።
5. "ታድናለህና (ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ) የተጠቃውን ሕዝብ።" ደሀ ወይም የተጠቃ ሕዝብ ከክፉ ሰዎች ጋር በተቃርኖ ተመልክቷል።
6. "ትዕቢተኞችን ዓይን ግን (ቢዲቢ 926፣ ኬቢ 1202፣ ቃል አንቀጽ፣ ኢሳ. 2፡11፤ 5፡15) ታዋርዳለህ" (ቢዲቢ 1050፣ ኬቢ 1631፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ)። ተቃርኗዊ ትይዩውን ተመልከት፣ ቁ. 27 ላይ ያለውን (2 ሳሙኤል 22 ትይዩ በመጠኑ ይለያል)።

ይህ አንጓ መሠረታዊውን መጽሐፍ ቅዱሳዊ እውነት ያስረግጣል፣ አንዱ/አንዷ የዘራውን እንደሚያጭድ (ኢዮብ 34:11፤ መዝ. 28:4፤ 62:12፤ ምሳ. 24:12፤ መክ. 12:14፤ ኤር. 17:10፤ 32:19፤ ማቴ. 16:27፤ 25:31-46፤ ሮሜ. 2:6፤ 14:12፤ 1 ቆሮ. 3:8፤ 2 ቆሮ. 5:10፤ ገላ. 6:7-10፤ 2 ጢሞ. 4:14፤ 1 ጴጥ. 1:17፤ ራዕ. 2:23፤ 20:12፤ 22:12)።

**18፡28-29** የቁ. 25-27 መልክ ቁ. 28-29 ላይ ተለውጧል። መዝሙረኛው በርካታ ማስረገጫዎች አድርጓል፣ ስለ ያህዌ ድርጊቶች።

1. ብርሃን ታበራለህ (ቢዲቢ 21፣ ኬቢ 24፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*) መብራቴን (ቢዲቢ 632፣ 2 ሳሙ. 22:29 "አንተ ብርሃኔ ነህ" የሚል አለው።
2. ያህዌ አምላኬ ያበራልኛል (ቢዲቢ 618፣ ኬቢ 667፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*)፣ ተመሳሳይ ትይዩነት ለግሦች) ጨለማዬ (ተቃራኒ ትይዩ የሆኑ ነገሮች፣ ማለትም፣ ብርሃን በተቃርኖ ጨለማ)።
3. ባንተ አሸንፋለሁ (ማለትም፣ ማሸነፍ) ሠራዊትን (ቢዲቢ 151 I፣ ማለትም፣ ወታደራዊ ጭፍራ)። አንዳንድ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች גדוד ይወስዳሉ (ቢዲቢ 151) *"መረማመጃ"* በሚለው ስሜት፣ እናም ሐረጉን እሱም "ቅጥሩን እዘልላለሁ" የሚለውን አቻ አድርገው ይተረጉማሉ፣ (የተእመቅ፣ አኢመቅ)። LXX (ማለትም፣ *አዲሱ የእንግሊዝና የሴፕቱዋጂንት ትርጉም* 2007) ፍጹም የተለየ ሐረግ ነው ያለው፣ "ባንተ ምክንያት ከዘራፊዎች ወጥመጥ ዳንኩ።" የ1970 የLXX ትርጉም ልማዳዊ ትርጉም አለው። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት "ጭፍራ" ሊለው ቃል "ሀ" ደረጃ ይሰጠዋል። 2 ሳሙኤል 22 ላይ ያለው ትይዩ ደግሞ ይኸው አለው።

   አመቅ የሚለው "ጭፍራ" ነው፣ እሱም እዚህጋ ብቻ የሚገኝ፣ ይኸውም "አውታር፣" גד፣ ደግሞም ከቀጣዩ ስንኝ ጋር ትይዩ የሆነ (ገጽ 114)።
4. በአምላኬ ቅጥሩን እዘልላለሁ። ቁጥር 3 እና 4 ተመሳሳዮች አይደሉም ነገር ግን ሁለት የተለያዩ መንገዶች ናቸው የእግዚአብሔርን ኃይል ማስታጠቅ ለማሳየት።

***መዝሙር : 18፡30-36***

**30የአምላኬ መንገድ ፍጹም ነው፥**
**የእግዚአብሔር ቃል የነጠረ ነው፥**
**በእርሱ ለሚታመኑት ሁሉ ጋሻ ነው።**
**31ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማን ነው?**
**ከአምላካችን በቀር አምላክ ማን ነው?**
**32ኃይልን የሚያስታጥቀኝ**
**መንገዴንም የሚያቃና፥**
**33እግሮቼን እንደ ብሖር እግሮች የሚያረታ**
**በኮረብቶችም የሚያቆመኝ እግዚአብሔር ነው።**
**34እጆቼን ሰልፍ ያስተምራል፥**
**በክንዴም የናስ ቀስት እገትራለሁ።**
**35ለደኅንነቴም መታመኛን ሰጠኸኝ፥**
**ቀኝህም ትረዳኛለች፥**
**ትምህርትህም ለዘላለም ታጠናኛለች፥ ተግሣጽህም ታስተምረኛለች።**
**36አረማመዴን በበታቼ አሰፋህ፥**
**እግሮቼም አልተንሸራተቱም።**

**18፡30-36** *ይህ አንጓ የሚያብራራው መዝሙረኛው ለያህዌ የቁ. 18፡2ን መጠሪያ ለምን እንደሰጠው ነው። የእርሱ ድርጊቶች መጠሪያዎቹን ያመጣሉ!*

1. *መንገዱ ፍጹም ነው* ("የተጠናቀቀ" ወይም "ፍጹም" ቢዲቢ 1071፣ ዝከ. ቁ. 23፣30፣32)።
2. *ቃሉ/ተስፋው* (ቢዲቢ 57፣ *መዝሙር* 119 ላይ 19 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል) *ተሞክሯል ወይም ተፈትኗል* (ቢዲቢ 864፣ ኬቢ 1057፣ *ቃል ተገብሮ አንቀጽ*፣ 2 ሳሙኤል 22፡31፤ *መዝሙር* 119፡140፤ ምሳሌ 30፡5)። ቪዲዮ ተመልከት "የእግዚአብሔር *ቃል ታማኝነት*" www.freebiblecommentary.org፣ ከባሕር ዳር ስብከቶች ባፕቲስት ቤተ ክርስቲያን፣ ዳላስ TX።
3. እሱ *ጋሻ* ነው (ቢዲቢ 171፣ ዝከ. 18:2)
4. እሱ *ዐለት* ነው (ቢዲቢ 849፣ ዝከ. 18:2)
5. እሱ *ያስታጥቀኛል* (ቢዲቢ 25፣ ኬቢ 28፣ *ፔል አንቀጽ*፣ ዝከ. 18:39) በኃይል (ቢዲቢ 298፣ የቢዲቢ 305 ተመሳሳይ፣ *መዝ*. 18:2 ላይ)
6. *መንገዴን ያቀናል* (ቢዲቢ 1071፣ ዝከ. 18:23፣30፣32)
7. *እግሮቼን ያበረታል* (ቢዲቢ 763፣ ኬቢ 840፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*) እንደ ብሖር እግሮች (ማለትም፣ ጸንቶ የሚቆም አጋዘን እሱም በገደላማና ድንጋያማ ስፍራዎች ያለ ችግር መራመድ የሚችል፣ ዕን. 3፡19)
8. እሱ *ያለማምደኛል/ያበቃኛል/ያስተምረኛል* ለጦርነት፣ *መዝ*. 144፡1
9. የማዳኑን *ጋሻ* ሰጥቶኛል፣ ዝከ. 18፡2
10. *ቀኝ እጁ ትደግፈኛለች*፣ *መዝ*. 63:8፤ 119:117 (ቀኝ እጅ የብርቱ ድርጊት ፈሊጥ ነው፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: እጅ *መዝ*. 7:3-4 ላይ)
11. *ቅነነቱ/ትሕትናው* (ኬቢ 855 II፣ ዝከ. 2 ሳሙ. 22:36፤ እንዲሁም ምሳ. 15:33፤ 18:12፤ 22:4 ተመልከት) ብርቱ አደረገኝ
12. እሱ *ያሰፋልኛል* (ቢዲቢ 931፣ ኬቢ 1210፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*) ርምጃዬን (ማለትም፣ 18:19ሀ፤ Ps. 4:1፤ 12:5፤ 31:8፤ 118:5 ጋር ትይዩ ነው)። ኒዶቴ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 317 መልካም ይዘት አለው፣ "ርግጠኛ መሆን የሚቻለው ሰፋ አድርጎ ሲታይ ደኅንነትን ሲያመለክት፣ ጠባብነት ደግሞ ለችግርና አደጋ ተምሳሌት ነው።"
13. እሱ የመዝሙረኛው እግሮች እንዳይንሸራተቱ አድርጓል (ቢዲቢ 588፣ ኬቢ 609፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ ማለትም፣ በመንገዱ ላይ እንዲቆይ፣ ዝከ. 18፡20-24፤ *መዝ*. 1፡1 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፣ ፍኖት/መንገድ)

**18፡30 "ከእግዚአብሔር በቀር አምላክ ማን ነው"** ይህ የአሀዳዊነት (አንድ አምላክ) ጠቃሽ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት *መዝ*. 2፡7 ላይ።

**18:35**

| | |
|---|---|
| ***አአመመቅ፣ አኪጀት*** | ***"ከብካቤህ"*** |
| ***አየተመት*** | ***"ረድኤትህ"*** |
| **ጄፒኤስአኤ** | **"ከብካቤህ"** |
| ***አአመመቅ፣ ጄፒኤስአኤ*** | |
| ***የግርጌ ማስታወሻ*** | ***"ራስን ዝቅ ማድረግ"*** |
| ***የተእመቅ፣*** **NAB** | ***"ዝቅ ማድረግ"*** |
| **LXX** | ***"ተግሣጽህ"*** |

የዕብራይስጡ *ሥር* "ራስን ዝቅ ማድረግ" ነው (ቢዲቢ 776፣ ቢዲቢ 776፣ ענה) ወይም "ዝቅ ማለት" (ቢዲቢ 776፣ ענו)። የቢዲቢ ሁለተኛውን አማራጭ ይደግፋል (አአመመቅ)፣ ነገር ግን ዩቢኤስ ጽሑፍ ፕሮጀክት የመጀመሪያውን አማራጭ "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ፣ አየተመት)።

***መዝሙር* ፡ 18፡37-42**

**37ጠላቶቼን አሳድዳቸዋለሁ እይዛቸዋለሁም፥
እስካጠፋቸውም ድረስ አልመለስም።
38አስጨንቃቸዋለሁ መቆምም አይችሉም፥
ከእግሬም በታች ይወድቃሉ።
39ለሰልፍም ኃይልን ታስታጥቀኛለህ
በበላዬ የቆሙትን ሁሉ በበታቼ ታስገዛቸዋለህ።
40የጠላቶቼን ጀርባ ሰጠኸኝ፥
የሚጠሉኝንም አጠፋሃቸው።
41ጮኹ የሚረዳቸውም አልነበረም
ወደ እግዚአብሔርም ጮኹ አልሰማቸውም።
42እንደ ትቢያ በነፋስ ፊት እፈጫቸዋለሁ፥
እንደ አደባባይም ጭቃ እረግጣቸዋለሁ።**

**18፡37-42** ይህ አንጓ የመዝሙረኛው ገለጻ ነው፣ ያህዌ እንዴት አድርጎ እንደረዳው/ኃይል እንዳስታጠቀው፣ ጠላቶቹን ድል እንዲያደርግ። እንደገናም፣ እነዚህ ጠላቶች እነማን እንደሆኑ ግልጽ አይደለም፣ ነገር ግን ቁ. 41 የሚያመለክተው እነርሱ የእስራኤል ሰዎች መሆናቸውን ነው (ማለትም፣ የሳኦል ሠራዊት፣ አቤሰሎም፣ ወይም ሌሎች ዐማጽያን)።

1. ጠላቶቼን አሳደድኳቸው
2. አሸነፍኳቸው
3. ወደ ኋላ አልተመለስኩም (ጠላቶቼ ግን አፈገፈጉ፣ ዝከ. ቁ. 40)
4. ሰባበርኳቸው
   ሀ. መነሣት አልቻሉም
   ለ. ከእግሬ በታች ወደቁ
5. በኃይል አስታጠቅኸኝ (ማለትም፣ ለተግባር አዘጋጀኸኝ) ለጦርነት
6. በበታቼ ታስገዛቸዋለህ (ማለትም፣ እንዲያጎነብሱ)
7. ጀርባቸውን ሰጠኸኝ
8. የጠሉኝን አጠፋኋቸው
9. እንደ ትቢያ እፈጫቸዋለሁ
10. እንደ አደባባይም ጭቃ ረግጣቸዋለሁ (2 ሳሙ. 22፡43፤ ሚኪያስ 7፡10)

አንዳንዶቹ የዳዊትን ድርጊቶች ሲገልጹ አንዳንዶቹም የያህዌን የማስቻያ ድርጊቶች እንደሚገልጹ ተመልከት።

**መዝሙር ፡ 18፡43-45**

**43ከሕዝብ ክርክር ታድነኛለህ፥**
**የአሕዛብም ራስ አድርገህ ትሾመኛለህ፥**
**የማላውቀው ሕዝብም ይገዛልኛል።**
**44በጆሮ ሰምተው ተገዙልኝ**
**የባዕድ ልጆች ደለሉኝ።**
**45የባዕድ ልጆች አረጁ፥**
**በመንገዳቸውም ተሰናከሉ።**

**18፡43-45** ይህ አንጓ የሚናገረው የእስራኤልን ንጉሥ የክብር ስፍራ ነው፣ በያህዌ ዕቅድ ለአሕዛብ ባለው። እስራኤል ("ሕዝብ" የቁ. 43ሀ) ማለት ለአሕዛብ የሚገልጽና ወደ ያህዌ ባለው እምነት የሚያመጣ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)። ነገር ግን እስራኤል "የሚስማማ" አልሆነም (መዝ. 35፡1)።

የተለያዩ ሐረጋትን ተገንዘብ፣ እስራኤላዊ ያልሆኑትን የሚያመለክቱን (ማለትም፣ አሕዛብ)።

1. የእስራኤል ንጉሥ (ዝከ. 18፡50) የአሕዛብ ራስ ተደርጓል
2. አሕዛብ ንጉሡ የማያውቃቸው ሕዝቦች ናቸው አሁን ግን ያገለግላሉ (ቢዲቢ 712፣ ኬቢ 773፣ ቃል ያልተጠናቀቀ) እሱን
3. እነዚህ አሕዛብ ንጉሡን እንደሰሙት
   ሀ. ይታዘዛሉ (ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ ኒፋል ያልተጠናቀቀ)
   ለ. ይገዛሉ ("መዋሸት" ወይም "መሸንገል" ነገር ግን ጥቅም ላይ የዋለው "ወደ ኋላ ማለት" በሚል ነው፤ ይልቁንም "ከቁጥር ማነስ" ወይም የቁጥራቸውና ተጽዕኗቸው ማነስ። የዕብራይስጡ ግሥ ሁለቱም መልኮች አሉት) — ቢዲቢ 471፣ ኬቢ 469፣ ፔይል ያልተጠናቀቀ
   ሐ. አረጁ — ቢዲቢ 615፣ ኬቢ 663፣ ቃል ያልተጠናቀቀ
   መ. መንቀጥቀጥ — ቢዲቢ 353፣ ኬቢ 350፣ ቃል ያልተጠናቀቀ፤ በብኪ እዚህጋ ብቻ፣ ከምሽጋቸው ውጪ — ("ስብ" ሊሆን ይችላል፣ ቢዲቢ 689፣ ወይም ኬቢ 604፣ "ወኅኒ፣" ሚክያስ 7፡17)

ያልተጠናቀቁት ሁሉ (ዘጠኝ) በሂደት ላይ ያለ ድርጊትን እንደሚገልጹ ተገንዘብ (ማለትም፣ ቀጣይነት ያለው ሽንፈት)።

**መዝሙር ፡ 18፡46-50**

**46እግዚአብሔር ሕያው ነው፥ አምላኬም ቡሩክ ነው፥**
**የመድኃኒቴም አምላክ ከፍ ከፍ ይበል።**
**47በቀሌን የሚመልስልኝ አምላክ**
**አሕዛብን በበታቼ ያስገዛልኛል።**
**48ከጠላቶቼ የሚታደገኝ እርሱ ነው**
**በእኔም ላይ ከቆሙ ከፍ ከፍ ታደርገኛለህ፥**
**ከግፈኛ ሰው ታድነኛለህ።**
**49አቤቱ፥ ስለዚህ በአሕዛብ ዘንድ አመሰግንሃለሁ፥**
**ለስምህም እዘምራለሁ።**
**50የንጉሡን መድኃኒት ታላቅ ያደርጋል፥**
**ቸርነቱንም ለቀባው ለዳዊትና ለዘሩ ለዘላለም ይሰጣል።**

**18፡46-50** ይህ አንጓ የመዝሙረኛው ለያህዌ ምስጋና ማቅረቢያ ነው፣ ስለ ባሕርዩ እና ድርጊቶቹ!

የያህዌን መጠሪያና ባሕርያት ተገንዘቡ።

1. ይኖራል — ይህ ቅጽል ነው (ቢዲቢ 311) እሱም ከ "መሆን" ግሥ የመጣ (ቢዲቢ 217)፣ እሱም የያህዌ ፍች የሆነ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:1 ላይ)። እሱ ዘላለማዊ ኗሪ ነው፣ ብቸኛው አንዱ ነዋሪ! ሐረጉ "ሕያው እግዚአብሔርን" ዘወትር የመሐላ መጀመሪያ ነው፣ እዚህ ግን የሚገልጸው እግዚአብሔርን ማክበሪያ ውዳሴ ነው።
2. ዐለቴ — ኃይልንና ጽኑዕነትን ይገልጻል (ዝከ. ቁ. 2፣ 31)
3. የደኅንነቴ አምላክ ( אלה )
4. በንጉሥ በኩል የእርሱ ድርጊት
   ሀ. በቀልን ይበቀልለታል (ቢዲቢ 668)
   ለ. ሕዝቦችን ያስገዛለታል
   ሐ. ያድናል (ዝከ. ቁ. 50)
   መ. ከጠላቶቹ በላይ ከፍ ያደርገዋል
   ሠ. ከግፈኛ ሰው ያድነዋል

ከዚህ አኳያ የእስራኤል ንጉሥ ምን እንደሚያደርግ ተገንዘቡ።

1. በአሕዛብ መካከል ምስጋና ያቀርባል
2. ለስሙ የምስጋና መዝሙር ያቀርባል

ንጉሥ ይሄንን የሚያደርግበት ምክንያት

1. በያህዌ ማዳን
2. ያህዌ ቸርነቱን በንጉሥ እና በዘሩ ላይ ለዘላለም ስለሚያደርግ (2 ሳሙኤል 7)

**18፡49** ይህ ቁጥር (ወይም 2 ሳሙ. 22፡50) በጳውሎስ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ሮሜ. 15፡9 ላይ፣ የያህዌን የመዋጀት ዕቅድ ለማሳየት፣ ገና ከመጀመሪያው አሕዛብ እንደተካተቱ (ዘፍ. 1:26-27፤ 12:3፤ ዘጸ. 19:5-6 ተመልከት)።

ደግሞም ጳውሎስ ዘዳ. 32:43፤ መዝ. 117:1 እና ኢሳ. 11:10ን ተጠቅሟል። ዘወትር ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ ለሰዎች ሁሉ ይኖራል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ፣ መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)።

**18፡50 "ለቀባው"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2፡2 ላይ።

▣ **"ቸርነት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 5፡7 ላይ።

▣ **"ለዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 9፡5 ላይ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የእግዚአብሔርን መጠሪያዎች ከቁጥር 2 ላይ ዘርዝር።
2. እግዚአብሔር ቁጥር 7-15 ላይ የተገለጸው እንደ ምንድነው?
3. ቁጥር 16-19ን እንዴት ትሰይመዋለህ?
4. ቁጥር 20 የሚያስተምረው "የጻድቅን ሥራ" ነውን?
5. "ዐለት" የሚለው መጠሪያ ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ የዋለው ከየት መጥቶ ነው? (ቁ. 2፣ 31፣ 46 እና ዘዳ. 32፡4፣31)
6. ቁጥር 43-45 ምን አንድምታ አለው?

## መዝሙር 19
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር ሥራ እና ቃል | የጌታ ፍጹም መገለጥ | ውዳሴ ለአምላክ ስለ ፍጥረታት ፈጣሪነቱና ሕግ ሰጭነቱ | የእግዚአብሔር ክብር በፍጥረት ላይ | ያህዌ፣ ፍትሕን የሚጠብቅ ልጅ |
| <u>ኤምቲ መግቢያ</u> ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር። | | | | |
| | | 19:1-4ሀ | | |
| | 19:1-4ለ | | 19:1-6 | 19:1-2 |
| 19:1-6 | | | | |
| | | | | 19:3-5 |
| | | 19:4ሐ-6 | | |
| | 19:4ሐ-6 | | | |
| | | | የጌታ ሕግ | 19:6 |
| | | 19:7-10 | | |
| | 19:7-11 | | 19:7-11 | 19:7 |
| | | | | 19:8 |
| | | | | 19:9 |
| 19:7-14 | | | | |
| | | | | 19:11-12 |
| | | 19:11-13 | | |
| | 19:12-13 | | 19:12-13 | |
| | | | | 19:13 |
| | | 19:14 | | |
| | 19:14 | | 19:14 | 19:14 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

*ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት*

ሀ. ይህ መዝሙር ሰዎች እንዴት እግዚአብሔርን እንደሚያውቁት ነው። ፈልገው ሊደርሱበት አይችሉም። እሱ ራሱን መግለጥ ይገባዋል፣ ሁለት መንገዶችም አሉት።

ለ. የእግዚአብሔር መገለጥ የግድ በግለሰብ ደረጃ የሚቀበሉትና የሚተገብሩት ሊሆን ይገባል! እሱ በቀዳሚነት የእምነት መግለጫ አልነበረም፣ ነገር ግን ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት እንጂ።

ሐ. ይህ መዝሙር ለሕይወቴ በሁለት መንገዶች ታላቅ ባርኮት ሆኖልኛል።
1. እሱ የቅዱስ ቃሉን የታመነ መሆንና የከበረነት ያመለክታል (ማለትም፣ ቁ. 7-10)
2. እሱ ተስፋና ሰላምን ይሰጣል፣ ከኃጢአት ጋር በየቀኑ በሚደረገው ትግል መካከል (ማለትም፣ ቁ. 11-14)

የቁጥር 14 ጸሎት አዘውትሬ የምጸልየው ነው!

መ. አጭር የፍሬ ሐሳብ ማውጫ

1. አጠቃላይ መገለጥ (እግዚአብሔር ራሱን በተፈጥሮ ይገልጣል፣ ቁ. 1-6፣ ሮሜ. 1፡19-20፤ ደግሞም ሮሜ 2፡14-15ን ተመልከት)
2. የተለየ መገለጥ (እግዚአብሔር ራሱን ገልጧል በሚያደርገው ነገር፣ ከስንኝ 2 ጋር ትይዩ)፣ እሱም መጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመዘገበ፣ ከፍ ባለ ደረጃም በልጁ፣ ቁ. 7-11፣ ዮሐንስ 1፡1-14፤ 14፡6፣9፤ 2 ቆሮ. 5፡17-21 (የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ሴሚናር ድረ-ገጽ መስመር ተመልከት www.freebiblecommentary.org፣ ላይ፣ እሱም አጠቃላይ የሥነ-ትርጓሜ አገባቦችና የተለዩ አገባቦችን ለተለያዩ ዘውጎች መረጃ የያዘ ነው)
3. የመማረክ ጸሎት፣ ቁ. 12-14

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 19፡1-6**

**1ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥**
**የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።**
**2ቀን ለቀን ነገርን ታወጣለች፥**
**ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች።**
**3ነገር የለም መናገርም የለም፥**
**ድምፃቸውም አይሰማም።**
**4ድምፃቸው ወደ ምድር ሁሉ፥**
**ቃላቸውም እስከ ዓለም ዳርቻ ወጣ።**
**5በእነርሱም ውስጥ የፀሐይን ድንኳን አደረገ፥**
**እርሱም እንደ ሙሽራ ከእልፍኙ ይወጣል**
**እንደ አርበኛ በመንገዱ ለመሮጥ ደስ ይለዋል።**
**6አወጣጡ ከሰማያት ዳርቻ ነው፥**
**ዞረቱም እስከ ዳርቻቸው ነው**
**ከትኩሳቱም የሚሰወር የለም።**

**19፡1 "ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥"** ይህ "የተፈጥሮ መገለጥ" በመባል ይታወቃል። ሮሜ 1፡19-20 ተመሳሳይ እውነትን ይገልጻል፣ እያንዳንዱ ሰው ስለ እግዚአብሔር አንዳች ነገር እንዲያውቅ፣ ከሥጋዊ ፍጥረት። ደግሞም ሮሜ. 2፡14-15 ተመልከት፣ እሱም ውስጣዊ የሞራል ምስክርነትን በሰዎች የሚያስረግጥ።

▣ **"ሰማያት"** መዝ. 8፡1፡ 50፡6 ተገንዘብ እንዲሁም ከሮሜ. 1፡19-20 ሥነ-መለኮትጋር እንዴት እንደሚዛመዱ። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2፡4 ላይ።

▣ **"ክብር"** ቢ.ዲ.ቢ. 458፣ ቁ. 2 ሐ፣ (2) ተመልከት።

### ልዩ ርዕስ፡ ክብር

የመጽሐፍ ቅዱሳዊው የ "ክብር" ጽንሰ ሐሳብ ለመግለጽ ያስቸግራል። የአማኞች ክብር፣ ከእግዚአብሔር የሆነውን የክብር ወንጌል ማወቅ ነው እንጂ በራሳቸው አይደለም (ዝኪ. 1፡29-31፤ ኤር. 9፡23-24)።

በብኪ. በጣም የተለመደው ለዕብራይስጥ ቃል ለ "ክብር" (ከብድ kbd) በዋነኛነት ከጥንድ ሚዛኖች ጋር የተያያዘ የንግድ ቃል ነው ("ከባድ መሆን")። ከበድ የሚል ዋጋ ያለውና የሚጠቅም ነው። የብሩኅነት ጽንሰ ሐሳብ በቃሉ ላይ ይታከልበታል የእግዚአብሔርን ግርማ ለማሳየት (ዘጸ. 19፡16-18፤ 24፡17፤ ኢሳ. 60፡1-2)። እሱ ብቻውን ጠቃሚና የሚከበር ነው። እሱ ለወደቀው የሰው ልጅ ለመድረስ ግሩም ነው (ዘጸ. 19፡16-18፤ 24፡17፤ ኢሳ. 6፡5)። ያህዌ በእውነት ሊታወቅ የሚችለው በክርስቶስ በኩል ብቻ ነው (ኤር. 1፡14፤ ማቲ. 17፡2፤ ዕብ. 1፡3፤ ያዕ. 2፡1)።

"ክብር" የሚለው ቃል አሻሚነትም አለው፡

1. ከ"የእግዚአብሔር ጽድቅ" ጋር ተነጻጻሪ ነው፤
2. እሱም ምናልባትም የሚያጣቅሰው ከእግዚአብሔር ቅድስና ወይም "ፍጹምነት" ጋር ነው፤ ወይም
3. የሰው ልጅ ከተፈጠረበት ከእግዚአብሔር አምሳል ጋር ያመላክታል (ዘፍ. 1፡26-27፤ 5፡1፤ 9፡6)፣ ነገር ግን ቆይቶ በዐመጽ ምክንያት ወደቀ (ዘፍ. 3፡1-22)። በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው በያህዌ መገኘት ከሕዝቡ ጋር በምድረ በዳ በሚዞሩበት ጊዜ፣ በዘጸ. 16፡7፣10፤ ሌዋ. 9፡23፤ እና ዘኍ. 14፡10።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“ጠፈር”** |
| **አኪጀት፣ አየተመት፣** | |
| **LXX** | **“ጠፈር”** |
| **አየተመት የግርጌ ማስታወሻ** | **“ሰማይ”** |
| **አኢመቅ፣ የተእመቅ** | **“የሰማያት ዳርቻ”** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **“ሰማይ”** |

ቃሉ (ቢዲቢ 956) ዘፍ. 1:6፣7 (ሦስቴ)፣8፣14፣15፣17 ጥቅም ላይ ውሏል። እሱም የሚገልጸው የዕብራይስጡን ጽንሰ-ሐሳብ የከባቢ አየርን ጠጣር ቅስት ወይም የተዘረጋ ቆዳ ነው (ማለትም፣ ድንኳን፣ መዝ. 104:2፤ ኢሳ. 40:22)። የሰማይ መስኮቶች መከፈት ይኖርባቸዋል ዝናቡ እንዲዘንብ።

“ሰማያት” ስንኝ 1 ላይ ከ “ጠፈር” ስንኝ 2 ጋር ትይዩ እንደሆነ ተገንዘብ።

▣ ***“የእጆችህን ሥራ”*** ይህ ሐረግ የሚያስረግጠው ያህዌ በፍጥረት ላይ ያለውን አካላዊ አገባብ ነው (ኢሳ. 48:13፤ 64:8)። እሱም በተለየ መልኩ የሚያንጸባርቀው የእርሱን አካላዊ የአዳም ፍጥረት ነው፣ ዘፍ. 2፡7 ላይ (ማለትም፣ “አበጀው” በመናገር ወደ ሕልውና ማምጣት ሳይሆን)።

**19፡2-3 *“ቀን ለቀን”*** የሁለቱም የ “ቀን” እና “ሌሊት” ሰውኛ ዘይቤ መሆን ተገንዘብ። ነጥቡ ፍጥረት ቀጣይነት ባለው መልኩ በዝምታ (ዝከ. ቁ. 3)፣ ስለ እግዚአብሔር መገለጥ/መልእክት መስጠቱ ነው (ማለትም፣ የዚህ ጽንሰ-ሐሳብ መልካም ዘመናዊ ማሳያ የሚሆነው “የጥበብ ንድፍ” እንቅስቃሴ ነው)።

**19፡2 *“ታወጣለች”*** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 615፣ ኬቢ 665፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ) መሠረታዊ ፍች አለው “አረፋ ያለው ምንጭ” (ምሳ. 18፡ 4)። እሱም በዘይቤነት ጥቅም ላይ እየዋለ የመጣው

1. በአዎንታ – መዝ. 19:2፤ 119:171፤ 145:7፤ ምሳ. 1:23
2. በአሉታ – መዝ. 59:7፤ 94:4፤ ምሳ. 15:28

▣ ***“ሌሊትም ለሌሊት እውቀትን ትናገራለች።”*** የሰው ልጅ ዘወትር በፍርሃት ይመለከታል፣ አንዳንዴም በጣዖት አምላኪነት፣ ኮከባቢውን ሰማይ (2 ነገ. 23:5፤ መዝ. 8:1፣3)።

**19፡3 *“መናገርም የለም”*** ይህ የሚያመለክተው የተፈጥሮን ዝምታ ነው፣ ነገር ግን ብርቱ ምስክር።

**19:4**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **“መልእክት”** |
| **አየተመት፣ ጀፒኤስአኤ** | **“ድምጽ”** |
| **አእቅ፣ አኢመቅ፣ የተእመቅ** | **“መልእክት”** |
| **LXX አአመመቅ ኅዳግ** | **“ድምጽ”** |
| **አእመቅ** | **“ዜማ”** |
| **ፔሺታ** | **“ቃላት”** |

ኤምቲ קַוָּם አለው (ቢዲቢ 876 II፣ ኬቢ 1081 ከ קַו)፣ እሱም “መለያ መስመር”ን “የዜማ ቃናን” የሚገልጽ (አእመቅ)። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት “ሀ” ደረጃ ይሰጠዋል። ሆኖም፣ LXX እና ጄሮም קֹלָם አላቸው (ቢዲቢ 876፣ ኬቢ 1083 ከקוֹל) ፍችውም “ንግግር፣” “ቃል፣” “ጩኸት፣” እሱም ከዐውዱ ጋር በተሻለ የሚገጥም (ተመሳሳይ ሥር ቁ. 3 ላይ ማለትም፣ ‘ድምጽ’)። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን የምትጠቀመው (ማለትም፣ የምትጠቅሰው) ከLXX ነበር።

▣ ***“ወደ ምድር ሁሉ፥ … እስከ ዓለም ዳርቻ”*** እነዚህ የመጀመሪያዎቹ ሁለት መስመሮች የቁ. 4 ተመሳሳይ ትይዩ ናቸው። ሥነ-መለኮታዊው ግፊት ሁሉን አቀፋዊ መገኘት ነው፣ የእግዚአብሔር መገለጥ ለሰዎች (ኢሳ. 42:10፤ 49:6፤ 62:11)። ሁሉም እግዚአብሔርን በማወቃቸው ኃላፊነት አለባቸው (ሮሜ. 1:18-3:18)።

የተፈጥሮ መገለጥ (ማለትም፣ በሥጋዊ ፍጥረት እና በውስጣዊ የሞራል ምስክር) መንፈሳዊ ኃላፊነትን ያመጣል፣ በሰዎች አኳያ ሁሉ ላይ (ሮሜ. 1፡18-3፡18)። አንድ ጊዜ ሰውየው ከዳነ ከዚያም በኋላ የማድነቅ፣ የምስጋና፣ እና የአምልኮ መንገድ ይሆንለታል፣ የፍጥረትን አምላክ (መዝሙር 8)።

**19፡4ሐ-6 *“ፀሐይ”*** ይህ ምናባዊ ምስያ ፀሐይን የተጠቀመው ሳይንሳዊ ገለጻ አይደለም፣ ወይም ሐተታ ተፈጥሮ፣ ነገር ግን የተለመደው የብኪ ቋንቋ ነው የታወቁትን ገላጭ ፈሊጦች የተጠቀመ፣ ለተፈጥሮ ክስተት። ምስያዎቹን ተገንዘብ።

1. ፀሐይ ድንኳን አለው (ማለትም፣ ማደርያ)፣ ቁ. 4ሐ
2. ፀሐይ ሙሽራ ነው፣ ቁ. 5ሀ
3. ፀሐይ ይራመዳል፣ የተወሰነውን ርቀት፣ ቁ. 5ለ (ማለትም፣ ቁ. 6 ላይ የተብራራ)

ፀሐይ በምድር ሁሉ ላይ እንደሚያበራ፣ እንዲሁ ደግሞ፣ የእግዚአብሔር ባሕርይ፣ ኃይል፣ ውበት፣ እና መልክ መገለጥ ሁለንተናዊ ነው (ዝኪ. ቁ. 4ሀ፣ለ)። እያንዳንዱ ሰው ስለ እግዚአብሔር አንዳች ነገር ያውቃል። ሌለኛው ብቸኛ ስፍራ "የተፈጥሮ መገለጥ" ከሥነ መለኮት አኳያ ጥቅም ላይ የዋለበት፣ የሰውን ኃላፊነት ለማመልከት የሚገኘው ሮሜ. 1፡18-3፡18 ላይ ነው።

ጳውሎስ ደግሞ ይሄንን ቁጥር በተለየ መልኩ ተጠቅሞበታል፣ ሮሜ. 10፡18 ላይ፣ ዓለም የእግዚአብሔርን መልእክት በክርስቶስ ማድመጥ/መቀበል እንደሚኖርበት በሚያመለክተው ዐውደ-ጽሑፍ (ማለትም፣ ወንጌል)። በጳውሎስ ዘመን የነበሩት ራቢዎች ዘወትር በርካታ ጥቅሶችን አንድ ላይ ይጠቀሙ ነበር፣ ነጥቡን ለማስቀመጥ። ጳውሎስ የሠለጠነው በደንብ (አገባብ) ነው።

መዝሙረኛው ፀሐይን ያነሣው እንደ ያህዌ አገልጋይ አድርጎ ነው፣ የፀሐይ አምልኮን ለመሄስ፣ የጥቅምን (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ)። ይህ መዝሙር፣ እንደ ዘፍጥረት 1 ሁሉ የሚያመለክተው ያህዌ ሰማያዊ አካላትን እንደፈጠረና እንደሚቆጣጠር ነው (ማለትም፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ፕላኔቶች፣ ተወርዋሪ ከዋክብት፣ ወዘተ)። እነርሱ አማልክት ወይም መላእክት አይደሉም፣ የሰውን ልጆች ሕይወት የሚቆጣጠሩ ወይም ይልቁንም ተጽዕኗቸውን የሚያሳርፉ!

**መዝሙር ፡ 19፡7-14**

**7የእግዚአብሔር ሕግ ፍጹም ነው ነፍስን ይመልሳል**
**የእግዚአብሔር ምስክር የታመነ ነው ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል።**
**8የእግዚአብሔር ሥርዓት ቅን ነው፥ ልብንም ደስ ያሰኛል**
**የእግዚአብሔር ትእዛዝ ብሩህ ነው፥ ዓይንንም ያበራል።**
**9የእግዚአብሔር ፍርሃት ንጹሕ ነው ለዘላለም ይኖራል**
**የእግዚአብሔር ፍርድ እውነትና ቅንነት በአንድነት ነው።**
**10ከወርቅና ከከቡር ዕንቍ ይልቅ ይወደዳል**
**ከማርና ከማር ወለላም ይጣፍጣል።**
**11ባሪያህ ደግሞ ይጠብቀዋል**
**በመጠበቁም እጅግ ይጠቀማል።**
**12ስሕተትን ማን ያስተውላታል? ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ።**
**13የድፍረት ኃጢአት እንዳይገዛኝ ባሪያህን ጠብቅ**
**የዚያን ጊዜ ፍጹም እሆናለሁ፥**
**ከታላቁም ኃጢአት እነጻለሁ።**
**14አቤቱ፥ ረድኤቴ መድኃኒቴም፥**
**የአፌ ቃልና የልቤ አሳብ**
**በፊትህ ያማረ ይሁን።**

**19፡7 "ጌታ"** ይህ የእግዚአብሔር፣ ያህዌ የኪዳን ስም ነው። እሱም ከዕብራይስጥ "የመሆን" ግሥ ነው፣ ዘጸ. 3፡14። ራቢዎች የሚሉት እሱ የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው፣ ከእስራኤል ጋር ባለው የተለየ ኪዳናዊ ግንኙነት። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡1 ላይ።

▣ **"ፍጹም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ነውር የሌለው መዝ. 18፡20-24 ላይ።

**19፡7-9 "ሕግ... ምስክር... ሥርዓት... ትእዛዝ... ፍርድ... ፍርሃት"** እነዚህ ለእግዚአብሔር የተጻፈ መገለጥ ተመሳሳዮች ናቸው። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡2 ላይ።

▣ **"ፍጹም... የታመነ... ቅን... ብሩህ... ንጹሕ... እውነት"** እነዚህ የእግዚአብሔር የተጻፈ መገለጥ ባሕርያት ናቸው። መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው፣ ግልጽ፣ የእግዚአብሔር የራሱ መገለጥ ነው። ይህ ዋነኛው የእምነት ማጽኛ ነው። እሱም በመሠረቱ "ተመስጦ" ተብሎ ይጠራል (ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት)። ለዚህ እምነት ቅድመ-ግምት ማስረጃዬን ለማግኘት ፍላጎቱ ካለህ "የአኪ ታማኝነት" የሚለውን በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር www.freebiblecommentary.org፣ "Video Sermons" "የቪዲዮ ስብከት፣" Lakeside፣ Dallas መመልከት ትችላለህ።

## ልዩ ርዕስ፡ ተመስጦ

የ"አንድ ጊዜ ለሁሉም" እምነት የሚያመለክተው እውነትን፣ መሠረተ-እምነቶች፣ ጽንሰ-ሐሳቦች፣ ዓለም-ተኮር የክርስትና ትምህርቶችን ነው (2 ጴጥ. 2፡21)። ይህ አንድ ጊዜ የተሰጠ አጽንዖት ከሥነ-መለኮት አኳያ ውስንነት ያለው መመሰጥ ነው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቅድመ-ግምት፣ ይህም ለአዲስ ኪዳን ጽሑፎች፣ እናም ኋለኞች ወይም ሌሎች ጽሑፎች ተመስጧዊ ሆነው እንዲቆጠሩ አይፈቅድም። በርካታ አሻሚ፣ ርግጠኛ ያልሆኑ፣ እና ግልጽ ያልሆኑ አካባቢዎች በአዲስ ኪዳን አሉ፣ ነገር ግን አማኞች የሚያስረግጡት

በእምነት "አስፈላጊ" የሆኑት ነገሮች፣ ለእምነትና ለተግባር በበቂ ግልጽነት በአዲስ ኪዳን መካተታቸውን ነው። ጽንሰ-ሐሳቡ "የመገለጥ ሦስት ማዕዘን" በሚባለው በግልጽ ተብራርቷል።

1. እግዚአብሔር ራሱን በታሪክ ጊዜና ቦታ ገልጧል (ራዕይ)
2. እሱም የተወሰኑ ሰዋዊ ጸሐፊዎችን መርጧል፣ ድርጊቶቹን ይመዘግቡና ያብራሩ ዘንድ (ተመስጦ)
3. እሱም መንፈሱን ሰጥቷል፣ የሰዎችን አዕምሮና ልብ ይከፍት ዘንድ፣ እነዚህን ጽሑፎች ያስተውሉ ዘንድ፣ በተወሰነ መልኩ ሳይሆን ለደኅንነት እና ለተሳካ ለክርስቲያን ሕይወት በቂ በሆነ መልኩ (ማብራሪያ)

የዚህ ነጥብ የሚሆነው ተመስጦ ለቅዱስ ቃሉ ጸሐፊዎች የተወሰነ መሆኑ ነው። ሌሎች ሥልጣን ያላቸው ተጨማሪ ጽሑፎች፣ ቅጅዎች፣ ወይም ራዕዮች አይኖሩም። ቅዱስ ቃሉ ተዘግቷል። የሚያስፈልጉን እውነቶች ሁሉ አሉን፣ ለእግዚአብሔር በተገቢው መልኩና በደስታ ምላሽ እንሰጥ ዘንድ።

ይህ እውነት በደንብ የሚታየው የመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፊዎች ስምምነትና፣ ቅን የሆኑ፣ መልካም አማኞች አለመግባባት ነው። ማንም ዘመናዊ ጸሐፊ ወይም ተናጋሪ የመለኮታዊ መሪነት ልኬት አለው፣ የቃሉ ጸሐፊዎች እንደነበራቸው ሁሉ።

**19:7-11 "ይመልሳል... ያደርጋል... ደስ ያሰኛል... ያበራል... ይኖራል... ፍርድ... ይወደዳል... ይጣፍጣል... ይጠብቀዋል... በመጠበቁም"** ይህ ነው የጽሑፍ መገለጥ ለእኛ የሚያደርገው። የቅዱስ ቃሉ ዋጋ ለወደቀው ሰው እንዴት ያለ ነው!

ሦስትዮሹን ትይዩዎች ተገንዘብ

| **የያህዌ መገለጥ መጠሪያዎች** | **የያህዌ መገለጥ መግለጫ** | **የያህዌ መገለጥ ዓላማ ወይም የሱ መግለጫ** |
|---|---|---|
| ቁ. 7ሀ የእግዚአብሔር ሕግ | ፍጹም/ነውር የሌለበት | ነፍስን ይመልሳል |
| ቁ. 7ለ የእግዚአብሔር ምስክር | የታመነ | ሕፃናትን ጠቢባን ያደርጋል (መዝ. 119፡98-100) |
| ቁ. 8ሀ የእግዚአብሔር ሥርዓት | ቅን | ልብንም ደስ ያሰኛል (መዝ. 119፡14) |
| ቁ. 8ለ የእግዚአብሔር ትእዛዝ | ብሩኅ | ዓይንንም ያበራል (መዝ. 36፡9፤ 119፡130) |
| ቁ. 9ሀ የእግዚአብሔር ፍርሃት | ንጹሕ | ለዘላለም ይኖራል |
| ቁ. 9ለ የእግዚአብሔር ፍርድ | እውነት | ቅንነት በአንድነት (ዘዳ. 32፡4፤ መዝ. 119፡138) |
| ቁ. 10ሀ እነርሱ | እጅግ የሚወደዱ | ወርቅ፣ ንጹሕ ወርቅ (መዝ. 119፡72፣ 127) |
| ቁ. 10ለ እነርሱ | ጣፋጭ | ማር፣ የማር ወለላ (መዝ. 119፡103) |
| ቁ. 11ሀ | እነርሱን መጠበቅ | ታላቅ ሽልማት |
| ቁ. 11ለ | ባሪያህ | ይጠብቃል |

እንዴት ያለው ጠንካራ ድግግሞሽና ትይዩነት ነው! የእግዚአብሔር መገለጥ የሚቤዥ፣ የሚያስረዳ፣ የሚያሳስብ፣ እና ርግጠኛ በረከት ነው! እግዚአብሔር ስለ መገለጡ ይመስገን!

**19:8-9 "ጽድቅ"** ይህ የዕብራይስጥ ሥር በዋነኛነት የሚለው "የመለኪያ ዘንግ" ነው። እሱም ስለ ፍርድ መስፈርት ነው የሚናገረው። እግዚአብሔር ራሱ ነው ያ መለኪያ። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡5 ላይ።

**19:9 "ፍርሃት"** ይህ አንስታይ ስም (ቢ.ዲ.ቢ. 432፣ ኬ.ቢ. 433) ፍችው "ማክበር" ወይም "በፍርሃትና በአክብሮት" ነው። ጽንሰ-ሐሳቡ ዘወትር በጥበብ ሥነ-ጽሑፍ ጥቅም ላይ ይውላል (ኢዮብ 4:6፤ 6:14፤ 22:4፤ 28:28፤ መዝ. 5:7፤ 34:11፤ 90:11፤ 111:10፤ 119:38፤ ምሳ. 1:7፤ 2:5፤ 8:13፤ 9:10፤ 10:27፤ 14:26-27፤ 15:16፤ 16:6፤ 19:23፤ 22:4፤ 23:17)። ተደጋጋሚው መልእክት ፍርሃት/አክብሮት/ማክበር የጥበብ መጀመሪያ መሆናቸው ነው! ያለ እግዚአብሔር እውነት አይኖርም፣ የወደቀው ሰው አስተያየት እና ወግ ካልሆነ በቀር (ኢሳ. 29፡13)።

▣ **"ለዘላለም ይኖራል"** ይኸው ተመሳሳይ እውነት በኢየሱስም ተገልጿል ማቴ. 5:18፤ 24:35፤ ማርቆስ. 13:31፤ ሉቃስ 21:33 ላይ።

**19፡10 “ከወርቅና... ከማር ይልቅ እጅግ ይወደዳል”** ይህ የአንተን ዝንባሌ በእግዚአብሔር መገለጥ ላይ ያለህን ይገልጻልን? መጽሐፍ ቅዱስህ እጅግ የተወደደ ሀብትህ ነውን?

**19፡11 “ባርያህም ይጠብቀዋል”** እግዚአብሔር ለሰላምና ደስታ ሕይወት መመሪያ ሰጥቶናል፣ ነገር ግን ልንኖርበት ይገባል! መለኮታዊ መንገድ አለ (መዝ. 1፡1 ላይ ማስታወሻ ተመልከት) በሱም ላይ መቆየት አለብን (ማቴ. 7፡13-14)።

**19፡12-13** እነዚህ ቁጥሮች እውቅና መስጫ እና ጸሎት ናቸው፣ ይኸውም አሁን ባለንበት ያለማወቅና የሞኝነት ሁኔታ መካከል ውስጥ እንኳ እግዚአብሔር በብቃት ሊሠራ እንደሚችል ነው፣ በወደቀው ተፈጥሯችን።

1. “ስሕተቱን ማን ያስተውላታል?” (መዝ. 40፡12)። እግዚአብሔር ብቻ ነው ልብን የሚያውቀው። እሱም መፍረድ ይኖርበታል (መዝ. 139:23-24፤ 1 ቆሮ. 4:4-5፤ ዕብ. 4:12-13)።
2. “ከተሰወረ ኃጢአት አንጻኝ።” ይህ የጸሎት ተተኳሪ ነው (ቢዲቢ 667፣ ኬቢ 720፣ ፔይል ተተኳሪ)። እሱም “የተሰወረ ጥፋት” እንደሆነ ተገንዘብ በግልጽ የሚታይ ዓመጻ ሳይሆን (ሌዋ. 4:2፣22፣27፤ 5:15-18፤ 22:14)።
3. “ከድፍረት ኃጢአት ጠብቀኝ” ይህ ሌላው ተተኳሪ ጸሎት ነው (ቢዲቢ 362፣ ኬቢ 359፣ ቃል ተተኳሪ)። ይህ ግልጽ የሆነ ዓመጸኝነት ነው።

   “ድፍረት” የሚለው ቅጽል (ቢዲቢ 267) መዝሙር 119 ላይ በርካታ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (ዝኬ. ቁ. 21፣ 51፣ 69፣78፣85፣122) እና “ትዕቢት” በሚል ነው የተተረጎመው፣ እሱም የዓመጸኝነት አዝማሚያን የሚያሳይ። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የሚገልጸው የሚታወቅ ኃጢአትን ነው።
4. “እንዳይገዙኝ” ይህ ግሥ ቃል ያልተጠናቀቀ ነው ነገር ግን በተጽዕኗዊ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። ይህም ሌለኛው የጸሎት ነጥብ ነው። ኃጢአት የባርያ-ገዥ ነው (ሮሜ. 5:21፤ 6:9፣14፣17፣23)።

የቁ. 13 የመጨረሻዎቹ ሁለቱ ስንኞች የመዝሙረኛውን ጸሎት ጥያቄ ውጤቶች ያሳያሉ።

1. ፍጹም እሆናለሁ
2. ከታላቁ ኃጢአትም እነጻለሁ

መዝሙረኛው በያህዌ ፍላጎትና ችሎታ ታላቅ እምነት አለው፣ ኃጢአትን ይቅር እንደሚልና እንደሚረሳ (ኢሳ. 1:18፤ 38:17፤ 43:25፤ 44:22፤ ሚኪያስ 7:19)። የዚህን ይቅርታ አገባብ የምንማረው በአዲስ ኪዳን ከተመዘገበው እና ከትርጓሜ ብቻ ነው፣ ከኢየሱስ ክርስቶስ ሕይወት፣ ትምህርት፣ ሞት፣ ትንሣኤ፣ ዕርገት፣ እና መመለስ (ማለትም፣ ወንጌል)። መዝሙር የእግዚአብሔርን የተጻፈ መገለጥ ድንቅና ታላቅነት እንደሚያከብር፣ አኪ ብቻ ደግሞ የእግዚአብሔርን ሥጋዌ መገለጥ ድንቅነት ይገልጣል (ማለትም፣ ሕያው ቃል)! ኢየሱስ የእግዚአብሔር የመዳረሻ መገለጥ ነው (ዮሐንስ 1:1-14፤ ቆላ. 1:13-17፤ ዕብ. 1:2-3)።

**19፡14** ከእግዚአብሔር መገለጥ ኃይል የተነሣ እና ከእርሱ አስደናቂ ይቅርታ አኳያ፣ መዝሙረኛው ጸሎቱን ቀጥሏል።

1. የአፌ ቃል (አንድ ግሥ፣ ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ይቆጣጠራል ቁ. 1፣2፣3)
2. የልቤ ሐሳብ
3. “ተቀባይነት ያግኝ” (ቢዲቢ 953) የሚለው
   ሀ. የተለመደ መሥዋዕታዊ ቃል ሌዋውያን ላይ
   ለ. እጅግ የተለመደ ቃል በጥበብ ሥነ-ጽሑፍ ላይ
   አዓት እሱን የሚተረጉመው እንደ
   1) የተደሰተ/የሚያስደስት/ደስታ
   2) የቀባይነት ያለው/ተቀባይነት ያገኘ
   3) ሞገስ/ሞገስ ያገኘ
   4) ብቁ የሆነ
   5) የደስታ

አንድ ጊዜ እሱን ካወቅንና በእርሱ ከተለወጥን፣ እሱን በሚያስደስት መንገድ ለመኖር እንሻለን። ሌሎችን ወደ እርሱ በሚያመጣ መንገድ። እውነተኛ ይቅርታ በመልካምነት በተለወጠ እና እየተለወጠ ባለ ሕይወት መገለጥ ይኖርበታል (ሮሜ. 8:28-30፤ 2 ቆሮ. 3:18፤ ገላ. 4:19፤ ኤፌ. 1:4፤ 4:13፤ 1 ተሰ. 4:3፤ 5:23፤ 2 ተሰ. 2:13፤ ቲቶ 2:14፤ 1 ጴጥ. 1:15)! የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት ግብ ስንሞት መንግሥተ ሰማይ አይደለም፣ አሁን ክርስቶስን መምሰል እንጂ!

◘ በርካታ ገላጭ መጠሪያዎች ይሄንን መዝሙር ይዘጉታል፣ መዝሙር 18ን እንደጀመሩት (ማለትም፣ ቁ. 2)።

1. ያህዌ (ማለትም፣ ዘላለም ኗሪ፣ ሁሉምጋ የሚገኝ፣ ብቸኛ አምላክ)
2. ዓለት
3. የሚቤዥ (ቃል አንቀጽ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ ከታች ያለውን)

## ልዩ ርዕስ፡ መዋጀት/ መቤዠት

1. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. በቀዳሚነት ሁለት የዕብራይስጥ የሕግ ቃላት አሉ፣ ይሄንን ጽንሰ-ሐሳብ የሚገልጹ።

1. *ጋል Ga'al*፣ እሱም በመሠረቱ "ነጻ ማውጣት" የሚል ፍቺ አለው፣ ዋጋ በመክፈል። ጎል የሚለው ቃል በቅርጹ ጽንሰ-ሐሳቡ ላይ ግላዊ ጣልቃ ገብነትን ይጨምራል፣ ዘወትር የቤተሰብ አባል (ማለትም፣ ተቤዢ ዘመድ)። ይህ ባህላዊ ገጽታ፣ ማለትም ዕቃዎችን፣ እንስሳትን፣ መሬትን መልሶ የመግዛት መብት (ሌዋውያን 25፥27)፣ ወይም ዘመዶችን (ሩት 4፥15፤ ኢሳ. 29፥22) ከሥነ መለኮት አኳያ የተሸጋገረው፣ የያህዌ እስራኤልን ከግብፅ መቤዠት ለማሳየት ነው (ዘጸ. 6፥6፤ 15፥13፤ መዝ. 74፥2፤ 77፥15፤ ኤር. 31፥11)። እሱም "ተቤዢ" ሆኗል (ኢዮብ 19፥25፤ መዝ. 19፥14፤ 78፥35፤ ምሳ. 23፥11፤ ኢሳ. 41፥14፤ 43፥14፤ 44፥6፣24፤ 47፥4፤ 48፥17፤ 49፥7፣26፤ 54፥5፣8፤ 59፥20፤ 60፥16፤ 63፥16፤ ኤር. 50፥34)።
2. *ፓዳህ Padah*፣ እሱም በመሠረቱ ፍችው "መታደግ" ወይም "ማዳን" ነው
   ሀ. የበኵር ልጅ መቤዠት፣ ዘጸ. 13፥13፣14 እና ዘኍ. 18፥15-17
   ለ. ሥጋዊ መዋጀት ከመንፈሳዊ መዋጀት በተቃርኖ ነው፣ መዝ. 49፥7፣8፣15
   ሐ. ያህዌ እስራኤልን ከኃጢአታቸውና ከዐመጻቸው ይዋጃቸዋል፣ መዝ. 130፥7-8

ለ. ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳቡ ሦስት ተያያዥ ነገሮችን ያካትታል።
1. ችግረኝነት፣ ባርነት፣ ኪሳራ፣ እስር ይኖራል።
   ሀ. አካላዊ
   ለ. ማኅበራዊ
   ሐ. መንፈሳዊ (መዝ. 130፥8
2. ለነጻነት፣ ለመለቀቅ፣ እና ለመመለስ ዋጋ መከፈል ይኖርበታል።
   ሀ. ለሕዝብ፣ እስራኤል (ዘዳ. 7፥8)
   ለ. ለግለሰብ (ኢዮብ 19፡25-27፤ 33፡28)
3. አንዱ እንደ ጣልቃ ገቢ እና ረድኤት መሥራት አለበት። በጋል ይህ ዘወትር የሚሆነው በቤተሰብ አባል ወይም በቅርብ ዘመድ ነው (ማለትም ጎል)።
4. ያህዌ ዘወትር ራሱን የሚገልጸው በቤተሰባዊ ቃላት ነው።
   ሀ. አባት
   ለ. ባል
   ሐ. የቅርብ ዘመድ ተቤዢ/ተበቃይ
   መቤዠት የሚጸናው በያህዌ አካላዊ ወኪልነት በኩል ነው፤ ዋጋ ይከፈላል፣ እናም መቤዠቱ ይቀዳጃል!

II. አዲስ ኪዳን

ሀ. ሥነ መለኮታዊውን ፅንሰ ሐሳብ ለመግለጽ በርካታ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል።
1. አጎራዞ *Agorazō* (1ኛ ቆሮ. 6፡20፤ 7፡23፤ II ጴጥ. 2፡1፤ ራዕ. 5፡9፤ 14፡3-4) ይህ የንግድ ቃል ነው፣ እሱም ለአንድ ነገር የተመለከተውን ዋጋ የሚያንጸባርቅ። እኛ በደም የተገዛን ሕዝቦች ነን፣ የገዛ ራሳችንን ሕይወት መቆጣጠር የማንችል። የክርስቶስ ነን።
2. አክሳጎራዞ *Exagorazō* (ገላ. 3፡13፤ 4፡5፤ ኤፌ. 5፡16፤ ቆላ. 4፡5)። ይህም ደግሞ የንግድ ቃል ነው። እሱም የሚያንጸባርቀው

3. የኢየሱስን የምትክ ሞት ነው፣ በእኛ ፈንታ። ኢየሱስ እርግማንን ተሸክሟል፣ በሕግ ተግባር ላይ የተመሠረተውን (ማለትም፣ የሙሴ ሕግ፣ ኤፌ. 2፡14-16፤ ቆላ. 2፡14)፣ እሱንም ኃጢአተኞቹ የሰው ልጆች መፈጸም የማይችሉት። እሱ እርግማንን ተሸከመ (ዘዳ. 21፡23) ለሁላችንም (ማርቆስ 10፡45፤ II ቆሮ. 5፡21)! በኢየሱስ፣ የእግዚአብሔር ፍትሕና ፍቅር ወደ ሙሉ ምሕረት፣ ተቀባይነት፣ እና ቀረቤታ ይወጣል!
4. ሉ፣ *Luō* "ነጻ ማውጣት"
   ሀ. ሉትሮን፣ *Lutron* "የተከፈለ ዋጋ" (ማቴ. 20፥28፤ ማርቆስ 10፥45)። እነዚህ ጠንካራ ቃላት ናቸው፣ ከኢየሱስ ከራሱ አንደበት የወጡ፣ የመምጣቱን ዓላማ በተመለከተ፣ የዓለም አዳኝ ለመሆን፣ የእሱ ያልሆነውን የኃጢአት ዕዳ ለመክፈል (ዮሐንስ 1፡29)።
   ለ. ሉትሮ፣ *Lutroō* "መልቀቅ"
      i. እስራኤልን መዋጀት፣ ሉቃስ 24፥21
      ii. ሕዝቡን ለመዋጀትና ለማጥራት ራሱን ሰጠ፣ ቲቶ 2፥14
      iii. ኃጢአት-የለሽ ምትክ መሆን፣ 1ኛ ጴጥ. 1፡18-19
   ሐ. ሉትሮሲስ፣ *Lutr ōsis* "መቤዠት፣ ማዳን፣ ወይም ነጻ ማውጣት"
      (1) የዘካርያስ ትንቢት፣ ስለ ኢየሱስ፣ ሉቃስ፣ 1፥68
      (2) የሐና ለእግዚአብሔር ምስጋና፣ ስለ ኢየሱስ፣ ሉቃስ 2፥38
      (3) የኢየሱስ የተሻለ፣ አንድ ጊዜ የቀረበ መሥዋዕት፣ ዕብ. 9፥12
5. አፖሊትሮሲስ *Apolytrōsis*
   ሀ. መዋጀት በዳግም ምጽአቱ (ሐዋ. 3፥19-21)
      (1) ሉቃስ 21፥28
      (2) ሮሜ 8፥23
      (3) ኤፌሶን 1፡14፤ 4፥30
      (4) ዕብራውያን 9፥15
   ለ. በክርስቶስ ሞት መቤዠት
      (1) ሮሜ 3፥24
      (2) 1ኛ ቆሮንቶስ 1፥30
      (3) ኤፌሶን 1፥7
      (4) ቆላስይስ 1፡14
6. አንቲሊትሮን *Antilytron* (1ኛ ጢሞ. 2፥6)። ይህ ወሳኝ የሆነ ጽሑፍ ነው (ቲቶ 2፥14 እንደሆነው)፣ መለቀቅን ከኢየሱስ የመስቀል

ላይ ምትክ ሞት ጋር የሚያያይዘው። እሱ አንዱና ብቸኛ ተቀባይነት ያለው መሥዋዕት ነው፤ ብቸኛው ስለ "ሁሉ" የሞተ (ዮሐንስ 1:29፤ 3:16-17፤ 4:42፤ I ጢሞ. 2:4፤ 4:10፤ ቲቶ 2:11፤ II ጴጥ. 3:9፤ I ዮሐንስ 2:2፤ 4:14)።

ሰ. ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳቡ በአዲስ ኪዳን የሚያመለክተው

1. የሰው ልጅ በኃጢአት ባርነት ተይዟል (ዮሐንስ 8፡34፤ ሮሜ. 3:10-18፤ 6:23)።
2. የሰው ልጅ የኃጢአት ባርነት በብኪ የሙሴ ሕግ ተገልጧል (ገላትያ 3) እና በኢየሱስ የተራራው ስብከት (ማቴዎስ 5-7)። የሰዎች ድርጊት የሞት ፍርድ ሆነ (ቆላ. 2፡14)።
3. ኢየሱስ፣ ነውር የሌለው የእግዚአብሔር በግ፣ መጥቶ በእኛ ምትክ ሞተ (ዮሐንስ 1፡29፤ 2ኛ ቆሮ. 5፡21)። ከኃጢአት የተገዛነው እግዚአብሔርን እንድናገለግል ነው (ሮሜ 6)።
4. በአንድምታ ያህዌም ሆነ ኢየሱስ "የቅርብ ዘመዶች" ናቸው፣ ለእኛ ብለው የሚሠሩ። ይህም ቤተሰባዊውን ዘይቤ ቀጣይ ያደርገዋል (ማለትም፣ አባት፣ ባል፣ ልጅ፣ ወንድም፣ የቅርብ ዘመድ)።
5. መቤዠት ለሰይጣን የተከፈለ ዋጋ አይደለም (ማለትም፣ መካከለኛው ሥነ-መለኮት)፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል እና የእግዚአብሔር ፍትሕ ከእግዚአብሔር ፍቅርና ሙሉ ሰጭነት ጋር በክርስቶስ የታረቁበት ነው። በመስቀል ሰላም ተመልሷል፣ የሰዎች ዐመጸኝነት ይቅር ተብሏል፣ የእግዚአብሔር አምሳል በሰው ልጆች አሁን በመሥራት ላይ ይገኛል፣ በወዳጃዊ ኅብረት!
6. ወደፊትም ቢሆን የመቤዠት ገጽታ ይኖራል (ሮሜ. 8፡23፤ ኤፌ. 1:14፤ 4:30)፣ እሱም የእኛን የሥጋ ትንሣኤና አካላዊ ወዳጅነትን ከሥላሴ (አምላክ) ጋር ያካትታል። የተዋጀው አካላችን የእሱን ይመስላል (1ኛ ዮሐንስ 3፡2)። እሱ አካል አለው፣ ነገር ግን ባለ ብዙ ኅብር ገጽታ። የ1ኛ ቆሮ. 15:12-19 ከ I ቆሮ. 15:35-59 ጋር ያለውን አያዎ (ፓራዶክስ) መግለጽ ያስቸግራል። ሥጋዊ፣ ምድራዊ አካል መኖሩ ግልጽ ነው፣ እንዲሁም፣ ሰማያዊ፣ መንፈሳዊ አካል ይኖራል። ኢየሱስ ሁለቱም አሉት!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "አጠቃላይ መገለጥ" ምንድነው? እሱስ ስለ እግዚአብሔር ምን ሊነግርህ ይችላል?
2. "በልዩ መገለጥ" ውስጥ ምን ተካትቷል? እሱስ ስለ እግዚአብሔር ምን ሊነግርህ ይችላል?
3. በዚህ መዝሙር ላይ ለእግዚአብሔር ሁለት የተለያዩ ስሞች ለምን ጥቅም ላይ ዋሉ?
4. ይህ መዝሙር እንደሚገልጸው በእግዚአብሔር ሕግ ብዙ ደስታ አግኝተህበታልን?
5. የሕግን ባሕርያት ዘርዝር።
6. ስለ ተሰወረ ኃጢአት ምን ማድረግ ይኖርብኛል?
7. "የድፍረት ኃጢአት" ምንድነው? በብኪ በእነርሱ ላይ እጅግ ጠበቅ የሚለው ለምድነው?
8. ቁጥር 14 ፍችው ላንተ ምን ማለት ነው?

## መዝሙር 20
## የአዲሶቹ ትርጕሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእት** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| በጠላቶች ላይ ድል ለመንሣት ጸሎት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ፡፡ የዳዊት መዝሙር፡፡ | የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ አስተማማኝነት | ጸሎት ንጉሥ በጦርነት ድል እንዲነሣ | የድል ጸሎት | ጸሎት ለንጉሥ |
| 20:1-3 | 20:1-3 | 20:1-3 | 20:1-5 | 20:1-2 |
| | | | | 20:3-4 |
| 20:4-5 | 20:4-5 | 20:4-5 | | |
| | | | | 20:5ሀ |
| | | | | 20:5ለ |
| 20:6-9 | 20:6 | 20:6-8 | 20:6-8 | 20:6 |
| | 20:7-8 | | | 20:7-8 |
| | 20:9 | 20:9 | 20:9 | 20:9 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ሦስተኛው አንቀጽ*
4. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

*ሀ. ይህ ሊሆን የሚችለው ወደ ጦርነት ከመሄድ በፊት የሚደረግ የአምልኮ ሥርዓት ነው፣ መዝሙር 21 ድል አድራጊው ንጉሥ እና ሠራዊት እንኳን ደኅና መጣህ እንደሚባል፡፡*

*ለ. ስጦታዎቹ የቁ. 3 (ማለትም፣ "ምግብ" እና "ስብ") የታወቁት መሥዋዕታዊ ስጦታዎች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ከውጊያ በፊት፡፡*

*ሐ. መዝሙር/ሆታ እና አርማዎች የቁ. 5 ድል አድራጊውን ንጉሥ እንኳን ደኅና መጣህ የማለቻ የተለመዱት መንገዶች ሊሆኑ ይችላሉ፡፡*
*መዝሙር 21 ከ20፡5 የተጠቀሰ መዝሙር ሊሆን ይችላል፡፡*

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 20፡1-3**
**[1]በመከራ ቀን እግዚአብሔር ይስማህ**

**የያዕቆብ አምላክ ስም ያቁምህ።**
**[2]ከመቅደሱ ረድኤትን ይላክልህ፥**
**ከጽዮንም ያጥናህ።**
**[3]ቍርባንህን ሁሉ ያስብልህ**
**የሚቃጠል መሥዋዕትህን ያለምልምልህ። ሴላህ**

**20፡1-3፤4-5** ይህ አንዳ ጸሎት ነው፣ ቁ. 4-5 ላይ እንዳለው፣ ወደ ያህዌ ለመለመን፣ የኪዳን ተወካዮቹን እንዲረዳ /ዳዊታዊውን ንጉሥ፣ 1 ሳሙ. 8:7፤ 10:19) በውጊያ ላይ (ዝከ. ቁ. 5፤7)፡፡

ተለጣጣቂ ያልተጠናቀቁትን ተገንዘብ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ (አአመመቅ፣ አየተመት፣ የተእመቅ፣ NIV፣ ጄፒኤስኦኤ፣ ማለትም፣ የጸሎት ጥያቄ) ቁ. 1-5 ላይ፡፡

1. እግዚአብሔር ይመልስልህ – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ ቃል ያልተጠናቀቀ
2. የያዕቆብ አምላክ ስም በከፍታ ላይ ይጠብቅህ – ቢዲቢ 960፣ ኬቢ 1305፣ ያልተጠናቀቀ
3. እሱ ከመቅደሱ ረድኤትን ይላክልህ – ቢዲቢ 1018፣ ኬቢ 1511፣ ያልተጠናቀቀ
4. እሱ ከጽዮን ይደግፍህ – ቢዲቢ 703፣ ኬቢ 761፣ ያልተጠናቀቀ
5. እሱ የእህል ቍርባንህን ሁሉ ያስብ – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ ያልተጠናቀቀ
6. እሱ የልብህን መሻትይስጥህ – ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 21:2፤ 37:4
7. እሱ ምክርህን/ዓላማህን ይፈጥምልህ – ቢዲቢ 569፣ ኬቢ 583፣ ፒይል ያልተጠናቀቀ
8. ልመናህን ሁሉ ይፈጽምልህ – እንደ ቁ. 7 ዓይነት

**20:1 "በመከራ ቀን"** ይህ ተደጋጋሚ ሐረግ ነው (ዘፍ. 35:3፤ 2 ነገ. 19:3፤ መዝ. 50:15፤ 77:3፤ 86:7፤ ምሳ. 24:10፤ 25:19፤ ኢሳ. 37:3፤ ኤር. 16:19፤ አብድ. ቁ. 12፤14፤ ናሆ. 1:7፤ ዕን. 3:16)፡፡ እሱም ለብዙ የተለያዩ የሕይወት ችግሮች ይቆማል፣ በዚህ በወደቀው ዓለም ለሚከሰቱ፡፡ ዜናው፣ እግዚአብሔር ችግሮቻችንን ሁሉ ማወቁ ነው /ማለትም፣ ዘጸ. 3፡7-8/ እናም በእነዚህ ችግሮች መካከል ከእኛ ጋር ነው፡፡ እሱ ለሰዎች ፍላጎት ሁሉ መልስ ነው፣ እንዲሁም በሚያስገርም መልኩ ይደግፈናል!

"ቀን" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 398) በርካታ ፍችዎች አሉት፡፡ ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ ዮም

የዮም (ቀን) ንድፈ ሐሳባዊ ትርጉም የተወሰደውና የተሻሻለው ከዶር. ጆን ሃሪስ (የክርስቲያን ጥናት ትምህርት ክፍል ዲንና የብኪ የምስራቅ ቴክሳስ ባፕቲስት ዩኒቨርሲቲ ፕሮፌሰር) የብኪ ጥናት 1 ማስታወሻ፡

1. የሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ንድፈ ሐሳብ በጥሬው
   ይህ ቀጥተኛ የሆነ አግባብ ነው (ዘጸ. 20፡9-11)። ከዚህ አግባብ የሚነሡት ጥያቄዎች፡
   ሀ. በመጀመሪያው ቀን ላይ እንዴት ብርሃን እንዴት ይኖራል፣ ፀሐይ እስከ አራተኛው ቀን ድረስ ካልተፈጠረች?
   ለ. ሁሉም እንሰሶች (በተለይም በሌለኛው የዓለም ክፍል በዋናነት የነበሩ) ከአንድ ቀን ባነሰ ጊዜ እንዴት ይሰየማሉ? (ዘፍ. 2፡19-20)?
2. የቀን ዕድሜ ንድፈ ሐሳብ
   ይህ ንድፈ ሐሳብ የሚሞከረው፣ ሳይንስን ኅብር ለመስጠት ነው (በተለይም ጂኦሎጂን) ለቃሉ ጋር። ይህ ንድፈ ሐሳብ የሚያሳየው "ቀናቱ" "ጂኦሎጂአዊ ዘመናት" መሆናቸውን ነው፣ በርዝመት። የእነሱም ርዝመት እኩል ነው፣ እንዲሁም እነሱ ጂኦሎጂን መልክ ለማስያዝ የተለያዩ ንብርብሮችን ግምት ለመግለጽ አገልግለዋል። ሳይንቲስቶች በዘፍ. 1 አጠቃላይ እድገት የመስማማት አዝማሚያ አሳይተዋል፡ ትነትና ውኃማ ክምችት የመሬትና የባሕርን መለየት መከተሉ፣ ከሕይወት በፊት መሆኑን ያሳያል። የእጽዋት ሕይወት ከእንስሳት ሕይወት በፊት ነው የመጣው፣ የሰው ልጅም የሚወከለው የኋለኛውንና ውስብስቡን የሕይወት ዓይነት ነው። በዚህ አግባብ ላይ የሚነሱት ጥያቄዎች፡
   ሀ. ዕጽዋት ያለ ፀሐይ "ለዘመናት" እንዴት ሊኖሩ ይችላሉ?
   ለ. በዕፅዋት ላይ የአበባ መዳቀል እንዴት ሊካሄድ ይችላል ነፍሳትና ወፎች "ለዘመናት" ሳይፈጠሩ ቆይተው ሳለ?
3. አማራጭ የቀናት ዕድሜ ንድፈ ሐሳብ
   ቀናቱ በርግጥ የሃያ አራት ሰዓት ጊዜ ነው ያላቸው፤ ግን፣ እያንዳንዱ ቀን በዘመናት ይከፋፈላል፣ ይህም የተፈጥሮን እድገት ያሳያል። በዚህ አግባብ ላይ የሚነሡ ጥያቄዎች፡
   ሀ. ተመሳሳይ የሆኑ ችግሮች ይነሣሉ፣ እንደ የቀን ዕድሜ ንድፈ ሐሳብ።
   ለ. ጽሑፉ "ቀንን" ያመለክታልን፣ እንደ ሃያ አራት ሰዓት እና እንደ ዘመናት ለመጠቀም?
4. ቀጣይነት ያለው የፍጥረት ጥፋት ንድፈ ሐሳብ
   ይህ ንድፈ ሐሳብ እንደሚከተለው ይራመዳል፡ በዘፍ. 1፡1 እና 1፡2 መካከል፣ ያልተወሰነ የጊዜ ሰዓት አለ፣ እሱም ጂኦሎጂያዊ ዘመናት የተከናወኑበት፤ በዚህ ጊዜ፣ ቅድመ ታሪክ ፍጥረታት በፎሲል የተገለጹት ተፈጥረዋል፤ በግምት ከ200000 ዓመት በፊት፣ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ ጥፋት ተከስቶ በዚህ ምድር ላይ ያለውን አብዛኛውን ሕይወት አጠፋ፣ እንዲሁም በርካታ እንስሳትን ደመሰሰ፤ ከዚያም የዘፍጥረት 1 ቀናት ተከሰቱ። እነዚህ ቀናት የሚያመለክቱት ዳግም ተፈጥሮን ነው፣ ከዋነኛ ተፈጥሮ ይልቅ።

5. የኤደን ብቻ ንድፈ ሐሳብ
የተፈጥሮ ሐተታ የሚያመለክተው በተፈጥሮ እና በአካላዊ ገጽታ ላይ ብቻ ነው፣ በኤደን ገነት።
6. የልዩነት ንድፈ ሐሳብ
በዘፍ. 1፡1 መሠረት፣ እግዚአብሔር ፍጹም የሆነ ዓለምን ፈጥሯል። በዘፍ.1፡2 መሠረት ሉሲፈር (ሰይጣን) በዓለም ጉዳይ ላይ ተከሶ ዐመጸ። እግዚአብሔርም ሊሲፈርንና ዓለምን በጽሑ ጥፋት ፈረደባቸው። ለሚሊዮን ዓመታት ዓለም ብቻዋን ቀርታ ነበር፣ እናም ጂኦሎጂያዊ ዘመናት አለፉ። በዘፍ. 1፡3-2፡3 መሠረት፣ በ4004 ቅ.ል.ክ ስድስት ጥሬአዊ ሃያ አራት ሰዓት ቀናት፣ ዳግም ተፈጥሮ ተፈጠረ። ቢሾፕ አሸር (1654 ዓ.ም) የዘፍጥረት 5 እና 11ን የትውልድ ዝርዝርን የሰው ልጅን ተፈጥሮ መች እንደሆነ ለማወቅ 4004 ዓ.ም ተጠቅመውበታል። ሆኖም፣ ጆኦሎጂ የተጠናቀቀ ቅደም ተከተላዊ ቀመርን አይወክሉም።
7. የተቀደሰው ሳምንት ንድፈ ሐሳብ
የዘፍጥረት መጽሐፍ ጸሐፊ የቀናትንና የሳምንታትን ጽንሰ ሐሳብ የተጠቀመው እንደ ሥነ ጽሑፋዊ መሣርያ ነው፤ ለእግዚአብሔር የፍጥረት ተግባር እንደ መለኮታዊ መለኪያ። እንዲህ ዓይነቱ መዋቅር የእግዚአብሔርን የፍጥረት ተግባር ውበትና የተለየ መልክ ያሳያል።
8. የኮስሚክ መቅደስ መመረቅ
ይህ የጆን ኤች. ዋልተንየቅርብ አተያይ ነው፣ የዘፍጥረት አንድ የጠፋው ዓለም፣ ቪአይፒ. 2009፣ እሱም ስድስቱን ቀናት የሚመለከታቸው እንደ፣ "ተግባራዊ ኦንቶሎጂ (ሥነ ሕላዌ) ነው እንጂ ቁሳዊ ኦንቶሎጂ አይደለም። እነሱ የሚያስረዱት፣ እግዚአብሔር ዩኒቨርስን ለሰው ልጆች ጥቅም ማዘዙን ወይም መሥራቱን ነው። ይህም ከሌለኛው ጥንታዊ ሥነ ትይንተ ዓለም (ኮስሞሎጂ) ጋር ይገጥማል። ለምሳሌ፣ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ቀናት የሚወክሉት እግዚአብሔር "ወቅቶችን (ማለትም፣ ጊዜን)፣ "የዓየር ሁኔታን" (ማለትም፣ ለአዝዕርት) እና ምግብን መስጠቱን ነው። የተደገመው ሐረግ "እሱም መልካም ነበር" ተግባራዊነቱን ይገልጻል። ሰባተኛው ቀን ሊገልጽ የሚችለው እግዚአብሔር ሞላውን ተግባሩንና ማደሪያ የሆነውን "ስነ ትዕይተ ዓለም (ኮስሚክ) መቅደስ፣ የራሱ ነብረት መሆኑን፣ ተቆጣጣሪና መሪ መሆኑን ያሳያል። ዘፍጥረት 1 ስለ ነገሮች ቁሳዊ አካል ተፈጥሮ አይደለም የሚገልጸው፣ ግን ለእግዚአብሔርና ለሰዎች ኅብረት የተግባር መገለጫ እንዲሆን ያለውን ሥርዓት ነው።
"ቀናቱ" የሆኑት ጽሑፋዊ የግንኙነት መሣርያ ነው፣ ለኤኤንኢ አጠቃላይ መግባባት፡
1. በተፈጥሯዊውና ከተፈጥሮ በላይ ለሆነው መካከል ምንም ልዩነት የለውም
2. መለኮት በሁሉም የሕይወት ገጽታ ውስጥ ገብቶ ነበር። የእስራኤል የተለየ መሆን የእሷ አጠቃላይ አተያይ አይደለም፣ የሚከተለው እንጂ
ሀ. የእሷ አሀዳዊነት
ለ. ተፈጥሮ ለሰው ልጅ እንጂ ለአማልክት አለመሆኑ
ሐ. በአማልክትና አማልክት እንዲሁም በአማልክትና በሰዎች መካከል በእስራኤል ደረጃ ግጭት አልነበረም።
እሷ የተፈጥሮዋን ድርሻ ከሌሎች አልተበደረችም፣ ግን የእነሱን አጠቃላይ የአለም አተያይ ተካፍላለች እንጂ።

◘ **"የያዕቆብ አምላክ ስም"** ይህንን ሐረግ የሚያብራሩ ሁለት ልዩ ርዕሶች አሉ፡፡
1. የመለኮት ስሞች መዝ. 1፡1 ላይ
2. የያህዌ ስም መዝ. 5፡11-12 ላይ

◘

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በከፍታ ላይ ይጠብቅህ"** |
| **አኪጀት** | **"ይከላከልልህ"** |
| **አየተመት፣ አእቅ፣ አኢመቅ፣ LXX** | **"ይጠብቅህ"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"በደኅንነት ይጠብቅህ"** |
| **የተእመቅ** | **"የብርታትህ ምሽግ ይሁንልህ"** |

የኤምቲ ግሥ (ቢዲቢ 960፣ ኬቢ 1305፣ ፒይል ያልተጠናቀቀ በተጽኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለው) "ከፍ ከማለት፣" ሥር ነው፣ እናም የማይደረስበትና ደኅንነቱ የተጠበቀ ነው (መዝ. 59፡1፤ 69፡29፤ 91፡14፤ 107፡41)፡፡ ይህም ተመሳሳይ የሆነ ምስያ ነው፣ ከፍ ላለ፣ መከላከያ ለሆነ ምሽግ፣ መዝ. 18፡2 ላይ ጥቅም ላይ የዋለ!

**20:2 "ከመቅደስህ... ከጽዮን"** እነዚህ የቅኔ ትይዩ ስንኞች ናቸው፡፡ ሁለቱም የሚያመለክቱት በኢየሩሳሌም ያለውን መቅደስ ነው፡፡ እሱም በዳዊት ጊዜ የተገነባ አልነበረም፣ ነገር ግን መቅደሱ እዚያ ነበር፡፡ ኢየሩሳሌም የተገነባችው በሰባት ተራራዎች ላይ ነበር፤ መቅደሱ የተገነባው በሞሪያ ተራራ ላይ ነበር (1 ዜና. 21፡18፤ 2 ዜና. 3፡1)፡፡ የጽዮን ተራራ በኢያቡስ ምሽግ ይዞታ ላይ ነበር፣ በዳዊት የተያዘው (ዝኪ. 2 ሳሙ. 5፡7፤ 1 ዜና. 11፡5)፣ እንዲሁም የቤተ-መንግሥቱ ይዞታ፡፡ ኋላ ላይም ስሙ ለመላው የኢየሩሳሌም ከተማ ጥቅም ላይ ዋለ፣ እናም "የጽዮን ሴት ልጅ" የሚለው ለእዝራኤላዊ ሕዝቦች (ዝኪ. 2 ነገ. 19፡21)፡፡
መዝ. 20፡6 የሚጠቀምበት ሐረግ "ከቅዱሱ የሰማይ ማደሪያው" እሱም ሌለኛው ትይዩ መሆኑን ተገንዘብ፡፡

**20፡3 «ሴላህ»** 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ እና መግቢያ ለመዝሙር VII ተመልከት፡፡

**መዝሙር ፡ 20፡4-5**

[4]እንደ ልብህ ይስጥህ
ፈቃድህንም ሁሉ ይፈጽምልህ።
[5]በማዳንህ ደስ ይለናል
በአምላካችን ስም ከፍ ከፍ እንላለን
ልመናህን ሁሉ እግዚአብሔር ይፈጽምልህ።

**20:4 "የልብህን መሻት"** ይህ የሰላምና የመታመን ጉዳይ ነው፡፡ የተገቢ መሻት መልካም ምሳሌ፣ ለዳዊታዊ ንጉሥ የሰሎሞን የመቅደስ ምርቃት ጸሎት ነው (1 ነገሥ. 8:22-61 ነው)፡፡

**20:5**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ስለ ደስታ እንዘምራለን"** |
| **አኪጀት፣ LXX** | **"እንደሰታለን"** |
| **አየተመት፣ አእቅ፣ ጀፒኤስአኤ** | **"በደስታ እንጮኻለን"** |
| **አኢመቅ** | **"በደስታ እናመሰግናለን…"** |
| **የተእመቅ** | **"ምስጋናህን ከፍ ባለ ድምጽ እንዘምር"** |

ይህ ግሥ (ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ ፒይል ተደጋጋፊ) "ጩኸትን" ይገልጻል፣ ለበጎ ወይም ለክፉ፣ በዐውደ-ጽሑፉ መሠረት፡፡ እዚህ በወታደራዊ ድል መደሰት ነው፣ በያህዌ በተገኘ (ሶፎ. 3:14)፡፡

◘ **"ከፍ ከፍ እንላለን"** ነገን ይከተለዋል (ቢዲቢ 186፣ ኬቢ 213፣ ቃል ያልተጠናቀቀ [በብኪ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው] በተደጋጋፊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ)፡፡ እሱም የሚጠበቅ የእንኳን ደኅና መጣህ ደንብ ነው፣ ለድል አድራጊ ንጉሥ እና ወታደራዊ፡፡

አእት መጽሐፍ ቅዱስ /ገጽ 875/ ማሻሻያ ያቀርባል፣ ለሌላ የግሥ ሥር ነኀጋ፣ ከቢዲቢ 162 ከመስተጸምር ጋር፡፡ አእት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ይህ ከትይዩው ጋር በተሻለ ይገጥማል፣ እንዲሁም መዝ. 89፡16 ያለው ማስታወሻ፣ ግሡ "በስምህ" ከሚለው ጋር ተያይዞ ጥቅም ላይ የዋለ፡፡

◘ **"ልመና"** ይህ የአልፎ አልፎ ስም /ቢዲቢ 982/ በብኪ ሁለቴ ብቻ ነው የሚገኘው፣ እዚህ እና መዝ. 37፡4 ላይ፡፡ የግሡ ሥር /ቢዲቢ 981/ ፍችው "መጠየቅ" ነው፡፡ ሥሩ በብዙ ስሞች ይከሰታል (1 ሳሙ. 9:2፣3፣5፤ 1 ዜና. 1:48፣49፤ 4:24፤ 6:24)፡፡

**መዝሙር ፡ 20፡6-9**

[6]እግዚአብሔር የቀባውን እንዳዳነው ዛሬ አወቅሁ
ከሰማይ መቅደሱ ይመልስለታል
በቀኙ ብርታት ማዳን።
[7]እነዚያ በሰረገላ እነዚያም በፈረስ ይታመናሉ
እኛ ግን በአምላካችን በእግዚአብሔር ስም ከፍ ከፍ እንላለን።
[8]እነርሱ ተሰነካከለው ወደቁ
እኛ ግን ተነሣን፥ ጸንተንም ቆምን።
[9]አቤቱ፥ ንጉሥን አድነው፥
በጠራንህም ቀን ስማን።

**20፡6-9** መዝሙረኛው /ማለትም፣ ንጉሡ፣ ካህን፣ ወይም የተከማቸ ነጠላ፤ ቁ. 9 በተሻለ ከዚህ የመጨረሻ አማራጭ ጋር ይገጥማል/ እምነቱን ያጸናል፣ ያህዌ በተገቢው ምላሽ እንደሚሰጠው፡፡

1. አሁን አወቅሁ — (ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ ቃል የተጠናቀቀ
2. ያህዌ ያድናል - ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ ሂፊል የተጠናቀቀ

ግሡ የሚገልጸው የተደላደለ መተማመንን ነው (መዝ. 56:9፤ 118:6፤ ሮሜ. 8:31-39)፡፡ ያህዌ በቀናነት ያደምጣል ይሰማልም /ዝከ. 20፡6ለ፣ሐ/፡፡ ንጉሡና የኪዳኑ ሕዝብ ሰፋ ያለው የመዋጀት ዕቅድ ክፋይ ናቸው፣ ለሰዎች ሁሉ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝሙር 2 መግቢያ ላይ/፡፡

**20:6 "የቀባውን"** ይህ የዕብራይስጥ ግሥ «መቀባት» ነው /ቢዲቢ 603/፣ እሱም የታወቀ መጠሪያ የሆነ፣ ለእግዚአብሔር የተለየው ለሚመጣው ንጉሥ /መዝ. 2፡2፤ 18፡50/፡፡ ልዩ ርዕሶችን ተመልከት

1. የብኪ መጠሪያዎች በተለየ ለሚመጣው መዝ. 2፡2 ላይ
2. «መሢሕ» መዝ. 2፡2 ላይ

◘ **"ቀኙ"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ኃይል፣ ሥልጣንን ለመጠቀም፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ መዝሙር 7፡3-4 ላይ፡፡

**20፡7** «*መመካት*» የሚለው ግሥ /ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ/ በጥሬው «የማስታወሻ ምክንያት» ማለት ነው፡፡ እሱም አንዱ የሚታመንበትን ያሳያል፡፡

1. የሰው ኃይል /ማለትም፣ ሠረገላ፣ ፈረሶች፣ ወታደሮች፣ ጦር መሣርያ፣ ወዘተ/
2. ያህዌና ተስፋዎቹ

እዚህጋ መልካም ትይዩዎች ጽሑፎች አሉ – ዘዳ. 20፡1፤ 31፡6፣8፤ መሳ. 7፡2፤ 1 ሳሙ. 17፡45፣47፤ 2 ዜና. 20፡17፤ 32፡8፤ መዝ. 33፡16፣ 17፤ 44፡2-3፣4-8፤ 60፡11-12፤ 146፡3-7፤ 147፡10፤ ምሳ. 21፡31፤ ኢሳ. 31፡3፤ ኤር. 17፡5፤ ዘካ. 4፡6! ምንድነው የምታምነው/የምትመካው?

◘ **"እንመካለን"** ግሡ /ቢዲቢ 209፣ ኬቢ 209፣ ሂፊል ያልተጠናቀ/ ፍችው «የማስታወሻ ምክንያት» ሲሆን እሱም ትርጉሙም ባለፈ ሁነት ወይም ባርኮት ወይም ግለሰብ መደሰት ወይም ማመስገን ነው፡፡ «*መመካት*» የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ጠቃሚ ነው፤ በተለይ ኤር. 9፡23-24 ተመልከት፡፡ የጽንሰ-ሐሳቡን አጠቃቀም በጳውሎስ ጽሑፎች ተመልከት፣ ከታች ባለው ልዩ ርዕስ፡፡

## ልዩ ርዕስ፡ መመካት

እነዚህ የግሪክ ቃላት *kauchaomai*፣ *kauchēma*፣ እና *kauchēsis*፣ ሠላሳ አምስት ጊዜ በጳውሎስ ጥቅም ላይ ሲውል፣ ሁለት ጊዜ ብቻ በቀሪው የአዲስ ኪዳን ክፍል ይገኛል (ሁለቱም በያዕቆብ)። የእሱ ዋነኛው አጠቃቀም በ1 እና 2 ቆሮንቶስ ላይ ነው።

ስለ መመካት ሁለት ዋንኛ እውነቶች ተያያዥነት አላቸው።

ሀ. ምንም ሥጋ መከበር/መመካት የለበትም፣ በእግዚአብሔር ፊት (1ቆሮ. 1፡29፤ ኤፌ. 2፡9)

ለ. አማኞች የግድ መኩራራት ያለባቸው በጌታ ነው (1ቆሮ. 1፡31፤ 2ቆሮ. 10፡17፣ እሱም ለኤር. 9፡23-24 ጠቃሽ ነው።

ስለዚህ፣ ተገቢ የሆነ እና ተገቢ ያልሆነ መመካት/መኩራራት አለ (ማለትም፣ ኩራት)።

ሀ. ተገቢ የሆነ

1. በክብር ተስፋ ላይ (ሮሜ 4፡2)
2. በእግዚአብሔር፣ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል (ሮሜ 5፡11)
3. በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል (ማለትም፣ የጳውሎስ ዋነኛ ጭብጥ፣ 1ቆሮ. 1፡17-18፤ ገላ. 6፡14)
4. ጳውሎስ የተመካው
   - ሀ. ማካካሻ በሌለው አገልግሎቱ (1ቆሮ. 9፡15፣16፤ 2ቆሮ. 10፡12)
   - ለ. በክርስቶስ በሆነው ሥልጣኑ (2ቆሮ. 10፡8፣12)
   - ሐ. በሌሎች ሰዎች ሥራ አለመመካቱ (አንዳንዶች በቆሮንቶስ እንደ ሆኑት፣ 2ቆሮ. 10፡15)
   - መ. በዘር ውርሱ (አንዳንዶች በቆሮንቶስ እንዳደረጉት፣ 2ቆሮ. 11፡17፤ 12፡1፣5፣6)
   - ሠ. በቤተ-ክርስቲያኖቹ
     - (1) ቆሮንቶስ (2ቆሮ. 7፡4፣14፤ 8፡24፤ 9፡2፤ 11፡10)
     - (2) ተሰሎንቄ (2ተሰ. 1፡4
     - (3) በእግዚአብሔር ማጽናትና መታደግ በነበረው መተማመን (2ቆሮ. 1፡12)

ለ. ተገቢ ያልሆነ

1. ከአይሁድ ውርስ ጋር በተዛመደ (ሮሜ. 2፡17፣23፤ 3፡27፤ ገላ. 6፡13)
2. አንዳንድ የቆሮንቶስ ቤተ-ክርስቲያን ይመኩ እንደነበረው
   - ሀ. በሰዎች (1ቆሮ. 3፡21)
   - ለ. በጥበብ (1ቆሮ. 4፡7)
   - ሐ. በነጻነት (1ቆሮ. 5፡6)
3. ሐሰተኛ መምህራን በቆሮንቶስ ቤተ-ክርስቲያን ሊመኩ ሞክረዋል (2ቆሮ. 11፡12)

**20፡8** ተቃርኗዊ ትይዩውን ተገንዘብ፡፡ ለቃላችን/ለድርጊታችን ውጤት አለ!

**20፡9 "ጌታ ሆይ፣ አድን"** ይህ አጽንዖታዊ የጸሎት ጥያቄ ነው (ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ* (መዝ. 3፡7፤ 6፡4፤ 17፡13)፡፡

◘ **"ንጉሥም በጠራነው ጊዜ ይስማን"** የግሡ ሰዋሰዋዊ መልክ ቃል ያልተጠናቀቀ ነው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ LXX እና በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች የሚመለከቱት ሕዝብ ለንጉሥ እንደሚያደርጉት ጸሎት ነው (ዝከ. 20፡6፤ መዝ. 21፡7፤ አየተመት፤ አእት፤ አኢመቅ፤ የተእመቅ) ወይም "ንጉሥ" ያህዌን ያመለክት ይሆናል (ታርጉምስ ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ 202፤ ደግሞም መዝ. 98፡6፤ 145፡1 ማስታወሻ ተመልከት)፡፡

# የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ሁሉንም የጸሎት ጥያቄዎች ዘርዝር በ "ያድርግ. . ." የሚጀምሩትን፣ ከቁጥር 1-5፡፡
2. «የልብህን መሻት ይስጥህ» ማለት ምን ማለት ነው?
3. ቁጥር 5 የሚያመለክተው ወታደራዊ ድል ነውን? ለምን?
4. የእግዚአብሔር "የተቀባው" ማነው?

## መዝሙር 21
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ስለ መታደግ ምስጋና<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር | ደስታ በጌታ ማዳን | ምስጋና ንጉሥ በጦርነት ድል ካደረገ በኋላ (ከመዝሙር 20 ትይዩ) | ምስጋና ለድል | ለንግሥና ክብረ-በዓል |
| 21:1-6 | 21:1-2 | 21:1-7 | 21:1-2 | 21:1-2 |
| | 21:3-4 | | 21:3-4 | 21:3-4 |
| | 21:5-7 | | 21:5-6 | 21:5-7 |
| 21:7-13 | | | 21:7-9ለ | |
| | 21:8-12 | 21:8-10 | | 21:8-10 |
| | | | 21:9c-12 | |
| | | 21:11-12 | | 21:11-12 |
| | 21:13 | 21:13 | 21:13 | 21:13 |

## የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)

### *የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙር 20 እና 21 ሳይያያዙ አይቀርም። መዝሙር 20 የአምልኮ ሥርዓት ጸሎት ነው፣ በጦርነት ድል በማድረግ፣ እንዲሁም መዝሙር 21 የአምልኮ ሥርዓታዊ አቀባበል ነው፣ ንጉሥ ከነሠራዊቱ በድል ስለተመለሰ።

ለ. ታሳቢዎቹን አንጓዎች ተገንዘብ። በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞችን የአንጓ ምድቦች በማነጻጸር አንድ ሰው ሊያስረግጥ ይችላል፣ ምን ያህል ዋነኛ እውነቶች በመዝሙሩ ውስጥ እንደተገለጹ።

1. አአመመቅ — 2
2. አኪጀት — 5
3. አየተመት — 4
4. አኢመቅ — 6

በግልጽ እንደሚታየው ርግጠኛ መሆን አስቸጋሪ ነው፣ እንዴት አድርጎ አንጓዎችን ለመለየት። ዘወትር ምንም ጽሑፋዊ ምልክት አይኖርም። ዘመናዊዎቹ ተማሪዎች የግድ

1. ትይዩዎችን ማስተያየት
2. የዕብራይስጡን የምት ፈርጅ ማስተያየት
3. ተጓዳኝ የሆኑ ርዕሰ-ጉዳዮችን ማስተያየት ይኖርባቸዋል (እያንዳንዱ አንጓ አንድ ዋነኛ ርዕሰ-ጉዳይ አለው)

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 21፡1-6**

**[1]አቤቱ፥ በኃይልህ ንጉሥ ደስ ይለዋል**
**በማዳንህ እጅግ ሐሤትን ያደርጋል።**
**[2]የልቡን ፈቃድ ሰጠኸው፥**
**የከንፈሩንም ልመና አልከለከልኸውም። ሴላህ**
**[3]በበጎ በረከት ደርሰህለታልና**
**ከክቡር ዕንቍ የሆነ ዘውድን በራሱ ላይ አኖርህ።**
**[4]ሕይወትን ለመነህ**
**ሰጠኸውም፥**
**ለረጅም ዘመን ለዘላለሙ።**
**[5]በማዳንህ ክብሩ ታላቅ ነው**
**ክብርንና ምስጋናን ጨመርህለት።**
**[6]የዘላለም በረከትን ሰጥተኸዋልና።**
**በፊትህም ደስታ ደስ ታሰኘዋለህ።**

**21፡1** ተመሳሳይ ትይዩውን ተመልከት "በኃይልህ" እና "በማዳንህ" መካከል ያለውን።

ቃሉ (ቢዲቢ 447፣ አንስታይ ጾታ) መዳንን የሚተረጉመው በበርካታ ታሳቢ ፍችዎች ነው።

1. ብልጥግና – ኢዮብ 30:15
2. መታደግ/ርዳታ – 2 ሳሙ. 10:11፤ 1 ዜና. 19:12፤ መዝ. 22:1
3. ማዳን – ዘፍ. 49:18፤ መዝ. 3:2፣8፤ 14:7፤ 35:3፤ 53:6፤ 62:2፤ እና ሌሎች በርካታ ተጨማሪዎች
4. ድል – ዘጸ. 15:2፤ መዝ. 20:6፤ 21:1፣5፤ 44:4፤ 68:20-21፤ 118:14፣15፣21

ያህዌ ታላቁ ተስፋችን ነው፣ ሌላ የለም! ከዚህ አኳያ፣ ታማኝ ተከታዮች፣ (በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ፣ ንጉሥ) ማድረጋቸውን ይቀጥላሉ

1. መደሰታቸውን – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1330፣ ቃል ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 9:2
2. መደሰት – ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189፣ ቃል ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 9:14

**21፡2** ይህ ቁጥር የሚያያዝ የሚመስለው ከመዝ. 20፡4 ጋር ነው፣ እናም ከንጉሥ ጸሎት ጋር ይያያዛል፣ ለወታደራዊ ድል።

ሁለቱን ትይዩ የተጠናቀቁ ግሦች ተመልከት (ማለትም፣ የተጠናቀቀ ድርጊት)።

1. ሰጠኸው — ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ ቃል የተጠናቀቀ
2. አልከለከልኸውም — ቢዲቢ 586፣ ኬቢ 602፣ አሉታዊ፣ ቃል የተጠናቀቀ

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመት** | **"ጥያቄ"** |
| **አኢመቅ** | **"ጸሎት"** |
| **LXX** | **"መሻት"** |
| **NEB** | **"ጥያቄ"** |

ቃሉ (ቢዲቢ 77፣ ኬቢ 92) በብኪ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው። ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ የሚጠቅስ የሚመስለው፣ የአምልኮ ሥርዓት ጸሎት ነው፣ ከጦርነት በፊት፣ ይኸውም በማደሪያው ድንኳን/በቤተ መቅደስ ሊሆን የሚችል።

▣ **"ሴላህ"** መዝ. 3፡2 ያለውን ማስታወሻ እና የመዝሙር መግቢያን ተመልከት፣ VII ላይ። አንዳንድ ተንታኞች የሚረዱት፣ እሱ የሚገልጸው በአምልኮ ሥርዓት ያለን ነጥብ ነው፣ እዚያም የሌላ አምልኮ ሥርዓት ድርጊት ትርጉም ያለበት (ማለትም፣ ምስጋና፣ መዝሙር፣ መሥዋዕት፣ ሌላ የአምልኮ ሥርዓት ንባብ፣ ስግደት፣ ወዘተ)።

**21፡3-6** እነዚህ የያህዌ ድርጊቶች ናቸው ከንጉሡ አኳያ።

1. በመልካም ነገሮች ባርኮት ተገናኘው (ማለትም፣ ያህዌ ራሱ ድል አድራጊውን ንጉሥ በደኅና ተቀበለው)
2. በራሱ ላይ የጥሩ ወርቅ አክሊል ደፋለት (ማለትም፣ የንግሥናው ዳግም ማረጋገጫ ወይም የአምልኮ ሥርዓታዊ ሽግግር፣ የጦርነት የራስ ቁሩ ወደ ንጉሣዊ አክሊል)
3. ስለ ሕይወት የለመነውን ጸሎት ሰጠው (ማለትም፣ በውጊያ ላይ ድል)
4. በእርሱ ላይ አኖረ
   ሀ. አስደናቂነትን (ቢዲቢ 217)
   ለ. ግርማ (ቢዲቢ 214) — እነዚህ የያህዌ መግለጫዎች ናቸው (1 ዜና. 16:27፤ መዝ. 45:3፤ 96:6፤ 104:1፤ 111:3)፣ ነገር ግን የያህዌ መልክ በሰው ልጅ ስለሆነ፣ እነዚህን ነገሮች ይጋራሉ (መዝ. 8፡5)
5. በረጅም ዕድሜ ባረከው (*'olam* የግድ መተርጎም የሚኖርበት በዐውደ-ጽሑፉ ነው፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9:5 ላይ፤ ጽሑፋዊ ትይዩው የሚሆነው "ንጉሥ ለዘላለም ይኑር" ነው 1 ሳሙ. 10:24፤ 1 ነገ. 1:25፣31፣34፣39፤ ዳን. 2:4፤ 3:9)
6. በመገኘትን ደስተኛ አደረግከው

ንጉሡ አይደለም የያህዌን ድርጊቶች የሚቀበለው፣ ነገር ግን በእርሱ በኩል ሁሉም የኪዳኑ ሕዝቦች እንጂ።

**መዝሙር ፡ 21፡7-13**

**[7]ንጉሥ በእግዚአብሔር ተማምኖአልና፥**
**በልዑልም ምሕረት አይናወጥም።**
**[8]እጅህ ጠላቶችህን ሁሉ ታግኛቸው፥**
**ቀኝህም የሚጠሉህን ሁሉ ታግኛቸው።**
**[9]በተቈጣህም ጊዜ እንደ እሳት እቶን አድርጋቸው**
**እግዚአብሔር በቍጣው ያጠፋቸዋል፥**
**እሳትም ትበላቸዋለች።**
**[10]ፍሬአቸውን ከምድር**
**ዘራቸውንም ከሰው ልጆች ታጠፋለህ።**
**[11]ክፋትን በአንተ ላይ ዘርግተዋልና፥**
**የማይቻላቸውንም ምክር አሰቡ።**
**[12]ወደ ኋላቸው ትመልሳቸዋለህ**
**ፍላጻን በፊታቸው ላይ ታዘጋጃለህ።**
**[13]አቤቱ፥ በኃይልህ ከፍ ከፍ በል**
**ጽናትህንም እናመሰግናለን እንዘምርማለን።**

**21፡7 "ንጉሥ በእግዚአብሔር ተማምኖአልና"** ይህ የንጉሥን እምነት ማረጋገጫ መግለጫ ነው (ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ ቃል የድርጊት አንቀጽ፣ መዝ. 4:5፤ 9:10፤ 13:5፤ 22:4፣5፣9፤ እና ሌላም ተጨማሪ)። ንጉሥ ብርታት፣ ደስታ፣ እና መታደግ አለው፣ በያህዌ ብቻ።

▣ **"በልዑሉ ምሕረት"** ልዩው የኪዳን ቃል፣ "ቸርነት" (ሄስድ፣ ቢዲቢ 338፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7 ላይ) ማለትም የያህዌ የኪዳነ ታማኝነት። ያህዌ ዘወትር ታማኝ ነው፣ ንጉሡና ሕዝቡም ደግሞ እንደዚሁ ይሆናሉ፣ "ማመናቸውን" እስከቀጠሉ ድረስ (ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120) በእርሱ (መዝ. 125፡1)። ነህምያ 9 ለያህዌ ታማኝነት እና ለእስራኤል ያለመታመን የተመዘገበ ነው!

ለ"ልዑሉ" (ኤሎሂም፣ ቢዲ 751) ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡1 ለ ላይ።

▣

**አአመመቅ፣ LXX፣**

| | |
|---|---|
| **ጄፒኤስኦኤ** | **"አይናወጥም"** |
| **አኪጀት፣ አየተመት** | **"አይነቃነቅም"** |
| **አእቅ** | **"ዘወትር ደኅንነቱ ይጠበቃል"** |
| **አኢመቅ** | **"እንዳይወድቅ ይጠብቀዋል"** |

ግሡ (ቢዲቢ 556፣ ኬቢ 555፣ ኒፋል ያልተጠናቀቀ) ፍችው "ተነቃናቂ፣" ወይም "የሚነቃነቅ፣" ወይም "ተንሸራታች" ማለት ነው። እሱም በብዙ መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል።

1. በዙፋን ላይ ማኖር
2. ደኅንነት በሕይወት
3. መልካም የሕይወት ስልት

የተለያዩትን መልኮች ለመመልከት፣ መዝ. 10:6፤ 15:5፤ 16:8፤ 21:7፤ 30:6፤ 62:2፣6፤ 112:6፤ ምሳ. 10:30፤ 12:3። በያህዌ መረጋጋት አለ፣ በወደቀው ዓለም ሳይሆን።

**21፥8-12** እነዚህ ቁጥሮች የሚገልጹት ያህዌ (ማለትም፣ በንጉሥ ሠራዊት በኩል) ምን እንደሚያደርግ ነው፣ ንጉሡና ሕዝቡ ታማኝ ሆነው እስከተገኙ ድረስ።

1. በጠላቶችህ ላይ ሥልጣን
2. ጠላቶችህ ይጠፋሉ
3. ጠላቶችህና ዝርያዎቻቸው ያልቃሉ ይጠፋሉም
4. ጠላቶችህ በዕቅዳቸው አይከናወንላቸውም (ማለትም፣ በያህዌ ንጉሥ እና በኪዳኑ ሕዝብ ላይ በክፉ ማቀድ በእግዚአብሔር ላይ ማቀድ ነው ዝኪ.ቁ. 1ሀ፤ መዝ. 2:1-3፤ 83:1-5)
5. ጠላቶችህ በጦርነት ወደ ኋላ ይሸሻሉ

አንዳንድ ሊቃውንት (AB ሀለ) እነዚህን ቁጥሮች የሚመለከቱት፣ ያህዌ እንዴት በጦርነት ላይ፣ ከኪዳኑ ንጉሥና ሕዝብ አኳያ እንደሚሠራ እንደሚገልጹ ነው።

◘ **"እጅ"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ድርጊትን ለመፈጸም ያለ ኃይል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ መዝ. 7፡3-4 ላይ።

**21፥9 "እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 118፣ ኬቢ 134፣ ፔይል ያልተጠናቀቀ) ለሙሉ ድምሰሳ ፈሊጥ ነው (ኢዮብ 2:3፤ 10:8፤ 19:3፤ 28:7፤ ሰቆ 2:2፣5፣8)።

**21፥13** ይህ ቁጥር መዝሙሩን የሚያጠቃልለው ለያህዌ በሚሆን ምስጋና ትእዛዝ ነው።

1. ከፍ በል – ቢዲቢ 926፣ ኬቢ 1202፣ *ቃል ተተኳሪ*። II ሳሙ. 22:47፤ መዝ. 18:46፤ 46:10፤ 57:5፣11፤ 108:5
2. እንዘምራለን – ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ *ቃል ተጓዳኝ*
3. እናመሰግናለን – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ *ፔል ተጓዳኝ*

◘ **"በኃይልህ"** ይህ ተደጋጋሚ ቃል መዝሙሩን ይጀምራል (ዝኪ. ቁ. 1) መዝሙሩን ይዘጋልም (ዝኪ. ቁ. 13)። እግዚአብሔር ዋነኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ገጸ ባሕርይ ነው። የእርሱ መጽሐፍ ነው፤ ስለ እርሱ ነው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙር 20 እና 21 እንዴት ይዛመዳሉ?
2. ቁጥር 4 የዘላለም ሕይወትን ያመለክታልን?
3. ቁጥር 7-13 ላይ ያሉትን ወታደራዊ ምስያዎች ዘርዝር።

## መዝሙር 22
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የኀዘን ልቅሶ እና የምስጋና መዝሙር <br>ኤምቲመግቢያ <br>ለመዘምራን አለቃ፤ ኤጄሊዝ ሃሸሻሀር ላይ። የዳዊት መዝሙር። | የመሢሑ መከራ፣ ምስጋናና ቀጣይ ዝርያ | ከገዳይ ሕመም ለመዳን ጸሎት (ሰቆቃ) | የኀዘን ልቅሶ እና የምስጋና መዝሙር | የጻድቅ መከራና ተስፋ |
| 22:1-5 | 22:1-2 | 22:1-2 | 22:1-5 | 22:1-2 |
| | 22:3-5 | 22:3-5 | | 22:3-5 |
| 22:6-8 | 22:6-8 | 22:6-8 | 22:6-8 | 22:6-8 |
| 22:9-10 | 22:9-11 | 22:9-11 | 22:9-11 | 22:9-11 |
| 22:11-18 | | | | |
| | 22:12-13 | 22:12-13 | 22:12-13 | 22:12-13 |
| | 22:14-15 | 22:14-15 | 22:14-15 | 22:14-15 |
| | 22:16-18 | 22:16-18 | 22:16-18 | 22:16-18 |
| 22:19-21 | 22:19-21ለ | 22:19-21ሀ | 22:19-21 | 22:19-21 |
| | 22:21ሐ | 22:21ለ-24 | | |
| 22:22-24 | 22:22-24 | | 22:22-24 | 22:22-23 |
| | | | | 22:24 |
| 22:25-31 | 22:25-26 | 22:25-26 | 22:25-26 | 22:25-26 |
| | 22:27-28 | 22:27-28 | 22:27-28 | 22:27-31 |
| | 22:29 | 22:29-31 | 22:29-31 | |
| | 22:30-31 | | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## *ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት*

*ሀ. ዘመናዊዎቹ ተርጓሚዎች የዋናውን ደራሲ ሐሳብ በጥብቅ ይወስዱ ዘንድ፣ ሥነ-ትርጓሜያዊ ትግበራ ይጠይቃል፣ የየትኛውንም ምንባብ ፍች በተገቢው ለመረዳት ይቻል ዘንድ እንደ ዋነኛ ነጥብ። ይህ በዚህ መዝሙር ላይ አስቸጋሪነቱን ያረጋግጣል።*

1. የኤምቲ መግቢያዎች ተመስጧዊነት ርግጠኛ አለመሆን (ማለትም፣ በሙት ባሕር ጥቅሎች ላይ አለመገኘት)
2. ዝርዝሮቹ ከንጉሥ ዳዊት ወይም ከሌላ የብኪ ሰው ሕይወት ጋር አለመግጠማቸው
3. ከኢየሱስ የመስቀል ላይ ልምምዶች ጋር አስደናቂ ተመሳሳይነታቸው (ማቴ. 27፡46፤ ማርቆስ 15፡34)

ለ. ስለዚህ፣ ዘመናዊዎቹ ተርጓሚዎች ይህን መዝሙር እንዴት ይመድቡታል?

1. ዐቢይ ምድብ (ማለትም፣ በብኪ ያለ አንድ ሁነት በኢየሱስ ሕይወት ላይ ካለ ሁነት ጋር ትይዩ መሆኑ)
2. ንግራዊ ትንቢት
3. ባለ ብዙ ፍጻሜ ትንቢት
4. ታሪካዊ ፍሬ-ሐሳብ (በቅኔ) የብኪ ሰው የሕይወት ልምድ

ሐ. በርካታ ያልተለመዱ ነገሮች ይኖራሉ፣ ከብኪ የመዝሙረኛው ታሪካዊ መቼት ጋር ሊታረቁ (ሊመሳከሩ) የማይችሉ።

1. ስቅለት (ማለትም፣ "የተወጋ" ማስታወሻ ተመልከት)
2. ልብሶችን በቁማር ጨዋታ በዕጣ መውሰድ
3. ያልፎ አልፎ ማስረገጫ፣ ለአሕዛብ መካተት፣ ቁ. 27
4. ታሳቢ ጠቃሾች
   ሀ. የዘላለም ሕይወት፣ ቁ. 26ሐ
   ለ. በሞቱት ላይ ያለው ተጽዕኖ፣ ቁ. 29
   ሐ. የታማኝ ተከታዮች "ዘር" መፈጠር፣ ለሚመጣው ትውልድ
5. ጠላቶችን ለመበቀል ወይም ለማጥቃት ጥሪ አለመደረጉን ተገንዘብ

መ. እኔም እንደ ሌሎቹ መዝሙርን የምቀርበው ከታሪካዊ፣ ሰዋሰዋዊ፣ ከሥርወ-ቃላዊ አኳያ ነው፣ ነገር ግን በአንድ ዓይን ወደ ክርስቶስ ሞት። ከዛ ያነሰ ማድረግ አልችልም!

ሠ. ይህ መዝሙር በአኪ የተጠቀሰው ወይም ጠቃሽነቱ ከኢየሱስ ስቅላት ጋር በተያያዘ ነው። አኪ ሁነኛው መነጽር ነው፣ ብኪን ለመመልከት፣ የተገላቢጦሹ ሳይሆን! አኪ (ማለትም፣ ኢየሱስ) የመዳረሻው መገለጥ ነው (ማቴ. 5፡17-48)።
1. ቁ. 1 – ማቴ. 27:46፤ ማርቆስ 15:34
2. ቁ. 7 – ማቴ. 27:39፤ ማርቆስ 15:29
3. ቁ. 8 – ማቴ. 27:43
4. ቁ. 16 – ማቴ. 27:35፤ ዮሐንስ 20:25
5. ቁ. 18 – ማቴ. 27:35፤ ማርቆስ 15:24፤ ሉቃስ 23:34፤ ዮሐንስ 19:24
6. ቁ. 22 – ዕብ. 2:12
7. በታሳቢነት ቁ. 15 – ዮሐንስ 19:28 ላይ

# የቃልና የሐረግ ጥናት

***መዝሙር ፡ 22፡1-5***

**1አምላኬ፥ አምላኬ፥ ለምን ተውኸኝ?**
**እኔን ከማዳንና ከጩኸቴ ቃል ሩቅ ነህ።**
**2አምላኬ፥ በቀን ወደ አንተ እጠራለሁ፥ አልመለስህልኝም**
**በሌሊትም እንኳ ዕረፍት የለኝም።**
**3በእስራኤል የተመሰገንህ አንተ ግን**
**በቅድስና ትኖራለህ።**
**4አባቶቻችን አንተን ተማመኑ፥**
**ተማመኑ አንተም አዳንሃቸው።**

[5]ወደ አንተ ጮኹ አመለጡም፥
አንተንም ተማመኑ አላፈሩም።

**22፡1** ተደጋጋሚ የቃና ለውጥ ያላቸው ዓረፍተ ነገሮች አሉ።

1. አምላኬ፣ አምላኬ፣ ቁ. 1 (መደገሙ ለአጽንዖት ነው)
2. አምላኬ ሆይ፣ ቁ 2 (ኤሎሀ፣ ቢዲቢ 43)
3. ጌታ ሆይ፣ 22፡19ሀ (ያህዌ፣ ቢዲቢ 217)
4. ረድኤቴ ሆይ፣ 22፡19ለ

መዘሙረኛው እግዚአብሔርን እየጠራ ነው፣ በቀጥታ አድራሻ፣ በተጠናከረ መልኩና በስሜት። እርስ በርስ ይተዋወቃሉ!

የዚህን መዝሙር የመጀመሪያ ክፍል ኢየሱስ በመስቀል ላይ መጥቀሱን ለማየት ያህል፣ እሱ እዚያ ላይ የሚለው (ወይም ተመስጧዊ የወንጌል ጸሐፊ) የወደፊቱ አንባብያን ሙሉውን መዝሙር እንዲያነቡ ነው። ከመጀመሪያው ስንኝ መጥቀስ ማለት የቅዱስ ቃሉን ጥቅል ዐውደ-ጽሑፍ መጥቀሻ መንገድ ነው።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**
**አየተመት፣ አኢመቅ** **"መተው"**
**አእቅ፣ ጀፒኤስአኤ** **"መተው"**

ይህ ግሥ (ቢዲቢ 736 I፣ ኬቢ 806፣ ቃል የተጠናቀቀ) ፍችው መተው ወይም መናቅ ነው፣ ርግፍ አድርጎ በመተው። የተጠናቀቀው የሚገልጸው የጸና መተውን ሐሳብ ነው። በበርካታ ስፍራዎች ብኪ ቃሉን የሚጠቀምበት፣ ያህዌ የኪዳን ሕዝቡንና ተስፋውን መተዉን ነው (መዝ. 119:8፤ ኢሳ. 54:7፤ ኤር. 7:12፤ ሕዝ. 8:12)፣ ነገር ግን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን ስለ ዘፍ. 28፡15 እና ስለ ኢሳ. 54፡7 ሁለተኛው ስንኝ።

የዚህን ችላ ማለት ወይም መተው ግላዊ ጽኑ ገጽታ ተገንዘብ (ማለትም፣ "እኔን፣" ማቴ. 27፡46)። መዝሙረኛው በያህዌ ተትቷል ችላ ተብሏልም። ለምን እንደሆነ አልተገነዘበም። እሱም በምንም ታሳቢ ኃጢአት አይደለም (ማለትም፣ በግድፈት ወይም በጥፋት)።

▣ ሁለተኛው ስንኝ ግሣዊነት የለውም። አኪጀት፣ አየተመት፣ የተእመቅ፣ ጀፒኤስአኤ ሁሉም "ስለምን…" የሚል ያክላሉ፣ እሱንም ጥያቄ የሚያደርጉት። መዝሙረኛው "ሲቃ" ይዞታል (ቢዲቢ 980፣ ኢዮብ 3:24፤ መዝ. 32:3)። የዕብራይስጡ ቃል ሊያመለክት የሚችለው የአንበሳን ግሳት ነው (ኢዮብ 4፡10)፣ ነገር ግን እዚህ የሰው ሲቃ ነው፣ የሥነ-ልቦናዊ እና አካላዊ ሥቃይ እና ምስቅልቅል፣ ይኸውም ለዚህ ዐውደ-ጽሑፍ በተሻለ የሚገጥም። መዝሙረኛው ሊገባው አልቻለም፣ ኪዳናዊው አምላክ ለምን ታማኙን የኪዳን ሰው ለተወው እንደቻለ (ዝከ. 22፡2)።

ይህ አስፈሪ የመተው፣ የብቸኝነት፣ እና መንፈሳዊ ምስቅልቅል ስሜት የውድቀት ውጤት ነው (ዘፍጥረት 3)። የሰው ልጅ፣ በያህዌ መልክና አምሳያ የተሠራ (ዘፍ. 1:26-27፤ 3:8)፣ ተጎድቷል። መገለል አስፈሪ ነው። በዚህ ሁኔታ የያህዌ ዝምታ ስሜት አጽንዖት ተሰጥቶታል፣ ምክንያቱም መዝሙረኛው እሱን ስለሚያውቀው። መዝሙረኛው ከእግዚአብሔር የሆነው ዝምታ ሊገባው አልቻለም፣ እንዲሁም ከሌሎች የሚደርስበት የጭካኔ ጥቃት! ነገር ግን ዓላማ ነበር (ማለትም፣ ወንጌል፣ ማርቆስ 10:45፤ 2 ቆሮ. 5:21)!

**22፡2** የመዝሙረኛው ጽኑ ጸሎት አለመሰማቱን ቀጥሏል፣ ወይም እሱ ቢያንስ ባጠቃላይ ምላሽ አልሰጠውም (መዝ. 42፡3፤ 88፡1-2)።

ሁለተኛው ስንኝ፣ የቁ. 2 ለመተርጎም አስቸጋሪ ነው። በጥሬው "ዝምታ አይኖረኝም" የሚል ነው። ይህ ማለት ሊሆን የሚችለው

1. ሌሊቱን ሁሉ ይጸልያል (አኪጀት፣ የተእመቅ)
2. እግዚአብሔር በዝምታው ቀጥሏል
3. ዕረፍት አላገኘም (LXX፣ አእት፣ ጀፒኤስአኤ)

ይህ የኢየሱስን ቀጣይ ልምምድ የሚያመለክት ከሆነ፣ እንግዲያውስ የመጨረሻው ምሽት በጌቴሴማኒ ያትክልት ስፍራ፣ ከመታሰሩ በፊት ያለው በተሻለ ይገጥመዋል (ማቴ. 26:36-46፤ ማርቆስ 14:32-42)።

**22፡3-5** መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይገልጻል እንደ

1. ቅዱስ (መዝ. 99፡9)
2. በእስራኤል ምስጋና ላይ በዙፋኑ ያለ (ማለትም፣ ያህዌ በኪሩቤል ክንፎች መካከል ይኖራል፣ ከኪዳኑ ታቦት በላይ፣ በቅድስተ ቅዱሳን)
3. በአባቶች የታመነ
   ሀ. እነርሱ ጸለዩ፣ እሱም አዳናቸው
   ለ. እነርሱ ተማመኑት፣ አላፈሩምም (ማለትም፣ ታሪካዊ ምሳሌ አለ፣ በያህዌ ለማመን

**መዝሙር ፡ 22፡6-8**
[6]**እኔ ግን ትል ነኝ ሰውም አይደለሁም**

**የሰው ማላገጫ በሕዝብም ዘንድ የተናቅሁ ነኝ።**
**7የሚያዩኝ ሁሉ ይላገዱብኛል**
**ራሳቸውን እየነቀነቁ በከንፈሮቻቸው እንዲህ ይላሉ።**
**8በእግዚአብሔር ተማመነ፥ እርሱንም ያድነው**
**ቢወድደውስ ያድነው።**

**22:6-8** ከ22:3-5 የተነሣ እና እግዚአብሔር በእርሱ ለሚታመኑት ካደረገው፣ ያለፈው የታማኝነት ድርጊቶች አኳያ፣ መዝሙረኛው ረድኤት እንደተደረገለት አልተሰማውም።

1. ራሱን እንደ ትል ቆጥሯል፣ ቁ. 6 (ኢዮብ 25:6፤ ኢሳ. 41:14)
2. እሱም ሰዎች ተሳልቀውበታል ንቀውታልም፣ ቁ. 6ለ
3. ይላገዱበታል፣ ቁ. 7 (ማቴ. 27:39፤ ማርቆስ 15:29)
4. በእምነቱና በጸሎቱ ላይ አሹፈዋል፣ ቁ. 8
   ሀ. ያድርግለት (“ጥቅል” መዝ. 37:5፤ ምሳ. 16:3) — ቢዲቢ 164፣ ኬቢ 193፣ ቃል ተተኳሪ (ማቴ. 27:43)
   ለ. ያድነው — ቢዲቢ 812፣ ኬቢ 930፣ ፔይል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ (ማቴ. 27:43)
   ሐ. ያድነው — ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

**መዝሙር ፡ 22:9-10**
**9አንተ ግን ከሆድ አውጥተኸኛልና፥**
**በእናቴ ጡት ሳለሁም በአንተ ታመንሁ።**
**10ከማኅፀን ጀምሮ በአንተ ላይ ተጣልሁ**
**ከእናቴ ሆድ ጀምረህ አንተ አምላኬ ነህ።**

**22:9-10** የእነዚህ ቁጥሮች ምናባዊ ምስያ ቀድሞ የተወሰነ ዓላማ ነው፣ የጻድቁ መከራ ተቀባይ አገልጋይ።

1. አንዳንድ ጊዜ አንድ ግለሰብ (ለመሢሑ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ኢሳ. 42:1 ላይ እና ለሞቱ ኢሳ. 52:13-53:12)
2. አንዳንድ ጊዜ የያህዌ ስብስብ ሕዝቦች (ኢሳ. 41:8-9፤ 42:18-19፤ 46:3፤ 49:1)

ይህ የብኪ የኪዳን ቋንቋ ነው። እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለውን የመዋጀት ዓላማ ለመግለጽ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)። መዝሙረኛው በእግዚአብሔር ዕቅድ ዓላማ እንዳለው አምኗል፣ እናም እግዚአብሔር ለምን የተወው እንደመሰለው አልገባውም (2 ቆሮ. 5:21)።

**22:10** ይህ ቁጥር የሚያንጸባርቀው በውልደት የኪዳንን ተቀባይነት ጽንሰ-ሐሳብ ነው (ማለትም፣ ግዝረት)። እስራኤላውያን የተወለዱት ከኪዳን ሕዝብ ነበር፣ ሆኖም፣ እውነተኛ የኪዳን እምነት እና ታዛዥነት የእምነታቸው ተጨባጭነት ማጽኛ ማስረጃ ነበር። ስለዚህ አብዛኞቹ እስራኤላውያን በርግጥ የኪዳን ሕዝብ አልነበሩም (ማለትም፣ ለኪዳን ስምምነቱ የማይታዘዙ፣ አመንዝራነት)!

**22:9**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ የተእመቅ** | **“አወጣኝ”** |
| **አኪጀት** | **“አወጣኝ”** |
| **አየተመት** | **“ወሰደኝ”** |
| **አኢመቅ፣ ጀፒኤስኦኤ** | **“መዘዘኝ”** |
| **LXX** | **“አወጣኝ”** |

ይህ አንቀጽ (ቢዲቢ 161፣ ኬቢ 189) በብኪ የተከሰተው እዚህጋ ብቻ ነው። ዐውደ-ጽሑፉ አጠቃላይ ስሜቱን ቢሰጠንም፣ ትክክለኛው ፍች ርግጠኛ ሳይሆን ይቀራል። ሆኖም፣ የግሡ አጠቃላይ ፍች ግልጽ ነው።

ያህዌ በሰው ሕይወት ውስጥ ይገባል፣ ከመወለድ በፊት እንኳ (ኢዮብ 31:11፤ መዝ. 139:13፤ መክ. 11:5፤ ኤር. 1:5)። ሕይወት የሚጀምረው በእግዚአብሔር ነው! ሰዎች የተፈጠሩት በእርሱና ለእርሱ ነው።

**መዝሙር ፡ 22:11-18**
**11ጭንቀት ቀርባለችና የሚረዳኝም የለምና**
**ከእኔ አትራቅ።**
**12ብዙ በሬዎች ከበቡኝ፥**
**የሰቡትም ፍሪዳዎች ያዙኝ**
**13እንደ ነጣቂና እንደሚጮኽ አንበሳ**
**በላዬ አፋቸውን ከፈቱ።**

[14]እንደ ውኃ ፈሰስሁ
አጥንቶቼም ሁሉ ተለያዩ
ልቤ እንደ ሰም ሆነ፥
በአንጀቴም መካከል ቀለጠ።
[15]ኃይሌ እንደ ገል ደረቀ፥
በጕሮሮዬም ምላሴ ተጣጋ፥
ወደ ሞትም አሸዋ አወረድሽኝ።
[16]ብዙ ውሾች ከብበውኛልና
የክፉተኞች ጉባኤም ያዘኝ
እጆቼንና እግሮቼን ቸነከሩኝ።
[17]አጥንቶቼ ሁሉ ተቈጠሩ
እነርሱም አዩኝ ተመለከቱኝም።
[18]ልብሶቼን ለራሳቸው ተከፋፈሉ፥
በቀሚሴም ላይ ዕጣ ተጣጣሉ።

**22፡11-18** ይህ የሚገልጸው የመዝሙረኛውን መከራ ምናባዊ ቅኔ ነው። አብዛኞቹ ቅኔያዊ ዝርዝሮች እና ትይዩዎች ኢየሱስን ለአለመቀበልና ለስቅለት እጅግ ጥሬአዊ በሆነ መልኩ ጥቅም ላይ ውለዋል።

**22፡11 "ከእኔ አትራቅ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 934፣ ኬቢ 1221፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ* ዝከ. 22:19፤ መዝ. 71:12) ጥቅም ላይ የዋለው በቅርብ ሰዋዊ መልኩ ነው፣ በራቀ መልኩ ሳይሆን። መዝሙረኛው ብቸኝነት ተሰምቶታል ("የሚረዳኝ የለምና፣" ኢሳ. 63፡5) ጠላቶቹን ለመግጠም (ማለትም፣ በሬዎች፣ አንበሶች፣ ውሾች፣ የዱር በሬዎች)። ተቃርኖውን ተገንዘብ— ችግር ሲቀርብ መዝሙረኛውም እግዚአብሔር እንዲቀርበው ይሻል!

**22:12-13፣16-18** ጠላቶቹ ተገልጸዋል።

1. በሬዎች ከብበውታል፣ ቁ. 12
2. አንበሶች አጥቅተውታል፣ ቁ. 13 (ማለትም፣ አፋቸውን በጣም ከፈቱ፣ እሱም ለአስከፊ ጥቃት ፈሊጥ የሆነ)
3. ውሾች ከብበውታል፣ ቁ. 16
4. እነርሱም አተኩረውበታል
5. እጅና እግሩን ቸንክረውታል (ዮሐንስ 20፡25፤ ከታች ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)
6. እነርሱ/አጥንቶቹን ሁሉ መቁጠር እችላለሁ (ማለትም፣ [1] በብኪ ይህ ሊያመለክት የሚችለው መከራን የተቀበለ ሰው ነው፣ ቆዳና አጥንት ብቻ እስኪቀረው ድረስ፣ [2] እሱ ሞቷል፣ በአራዊት ተበልቶ፣ አጥንቱ ብቻ ነው የቀረው ወይም [3] በአኪ ይህ የሚያመለክተው የሁለቱ ሌቦች እግር የተሰበረበትን ዝርዝር ነው፣ ሞታቸውን ለማፋጠን በመስቀል ላይ፣ ኢየሱስ በዚህ ሰዓት ሞቶ ነበር)
7. እነርሱም ልብሶቹን ዕጣ በመጣጣል ተከፋፈሉ (ማቴ. 27:35፤ ሉቃስ 23:34፤ ዮሐንስ 19:24)

**22፡14-15** ይህ እጅግ ዘይቤአዊ ቋንቋ ነው። ትክክለኛውን ጠቃሽ ነቅሶ ማውጣት አይቻልም፣ ነገር ግን ድምር ውጤቱ ሙሉ ለሙሉ ያልተበረታታ ሰው ነው

1. በያህዌ አጠቃላይ ዝምታ፣ ምንም እንኳ መዝሙረኛው ቀን ከሌት ቢያለቅስም/ቢያጣጥርም
2. በሁሉም በኩል የግፈኛ ጠላቶቹ መገኘት
3. ምናባዊ ምስያው የሚጠቅሰው የሕመም ምልክትን ይመስላል (ኢሳ. 52፡14) ወይም ከሞት በፊት የሆነ የሰውነት የመበስበስ ሂደት (ማለትም፣ "አጥንቶች የተበታተኑ" ቢዲቢ 825፣ ኬቢ 962)

የሚነካ፣ የሚያም፣ የሚያስገርም ስሜት ከታማኝ የኪዳን ተከታይ!

**22:15**

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **RSV፣ LXX** | **"ኃይል"** |
| **አየተመት፣ አኢመቅ፣** | |
| **የተእመቅ** | **"አፍ"** |
| **አእቅ** | **"ጉሮሮ"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"ኃይል"** |

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ለኤምቲ "ኃይሌ" (כחי) "ሀ" ደረጃ ይሰጠዋል (ከፍተኛ የመሆን ዕድል)። አአመት፣ አኢመቅ፣ የተእመቅ፣ እና አእት ተናባቢዎቹን የተገላቢጦሽ ያደርጓቸዋል፣ "ጉሮሮዬ"ን ለመፍጠር (חכי ኬቢ 313፣ ኢዮብ 12:11፤ 20:13፤ መዝ. 119:103፤ 137:6፤ ሰቆ. 4:4፤ ሕዝ. 3:26)።

◘
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመት** | ***"መንጋጋ"*** |
| **የተእመቅ** | ***"ድድ"*** |
| **አእቅ** | ***"ትናጋዬ"*** |
| **አኢመቅ** | ***"መንጋጋ"*** |
| **ጀፒኤስአኤ** | ***"ጉሮሮ"*** |
| **LXX** | ***"ጉሮሮ"*** |

ይህ የዕብራይስጥ ቃል (ቢዲቢ 544 II፣ ኬቢ 594) እዚህጋ ብቻ ነው በብኪ የሚከሰተው። ስለዚህ፣ ዐውደ-ጽሑፍ፣ ትይዩነት፣ እና ተዛማጅ ሥሮች ለተርጓሚዎች ተገቢውን ፍቺ ሊሰጡ ይገባል። ነገር ግን እባካችሁ ተገንዘቡ፣ የዚህን ቃል ትክክለኛ ፍች ባናውቀውም፣ የቁጥሩ አጠቃላይ ስሜት ግልጽ ነው።

**22፡15 "ወደ ሞትም አሸዋ አወረድኸኝ።"** "አንተ" እዚህ የሚያመለክተው ያህዌን ነው። ያህዌ (ማለትም፣ ብቸኛው መነሻ፣ በዩኒቨርስ) መዝሙረኛው ሞትን እንዲያይ ፈቀደ (ማለትም፣ ያልተጠናቀቀ ግሥ፣ መዝ. 104፡29)። ይህም ከአኪ መረዳት ጋር ይገጥማል፣ ከኢየሱስ የተለዋጭነት መከራ፣ የተቀያሪነት ሞት፣ እኛን ተክቶ፣ በያህዌ ቀዳሚ ፍቃድ መሠረት (ሉቃስ 22:28፤ ሐዋ. 2:23፤ 3፡18፤ 4:28፤ 1 ጴጥ. 1:20)።

ኢየሱስ ሥጋን የለበሰው ለብዙ ዓላማዎች ነው።

1. አብን በሙላት ለመግለጥ
2. የእርሱን የመዋጀት ዕቅድ በሙላት ለመግለጥ (ማለትም፣ ወንጌል)
3. በእኛ ምትክ ለመሞት፣ ለኃጢአታችን
4. ሰዎች ለምን ተፈጥረው እንደነበር ሊያሳየን

እነዚህን ቀጥተኛ ያልሆኑ የብኪ ጽሑፎች መተርጎም ዋነኛ ነገር ነው፣ ሙሉውንና የተጠናቀቀውን የአኪ መገለጥ ለመመልከት። አኪ የብኪ የተጠናቀቀ ፍጻሜ ነው (ማቴ. 5፡17-48)። ታሪኩን ሙሉ ለሙሉ መረዳት የሚቻለው በኢየሱስ በመሢሑ ብቻ ነው!

**22፡16**
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **የተመት** | **"ቸነከሩኝ"** |
| **አየተመት** | **"መጠውለግ" (የአካድያን ሥር)** |
| **አእቅ** | **"መቅደድ"** |
| **LXX** | **"መውጋት" ወይም "መቆፈር"** |
| **አኢመቅ፣ NEB** | **"መቁረጥ"** |
| **ጀፒኤስአኤ (cf. Isa. 38:13)** | **"እንደ አንበሶች (እነርሱ አቆሰሉኝ፣ ዝከ. ቁ. 13)"** |
| **የተእመቅ (ግርጌ ማስታወሻ)** | **"ማሰር"** |
| **አእት መጽሐፍ ቅዱስ** | **"እንደ አንበሳ ይወጋሉ"** |

ይህ ቁጥር በቀጥታ አልተጠቀሰም፣ በአኪ ወንጌላት፣ ከኢየሱስ ስቅለት ጋር በተያያዘ። በርካቶቹ የዚህ መዝሙር ቁጥሮች ግን ተጠቅሰዋል። ርግጠኛው ጥያቄ የሚሆነው፣ "ዕብራይስጡ ምን ይላል?" ነው።

1. የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት "እንደ አንበሳ" የሚለው ( יְרִאֲכּ ፣ ቢዲቢ 71) "ለ" ደረጃ ይሰጣል።
2. "መቆፈር፣" "መማስ፣" ወይም "መውጋት" የሚለው ግሥ የመጣው ከ כּוּר ነው፣ ቢዲቢ 468 II (እዚህጋ ብቻ የሚገኝ)።
3. "ማሰር" ወይም "ሸብ ማድረግ" የመጣው ከግሪክ ትርጉም ነው፣ ከአቂላ፣ ሲማቹስ፣ ከጀሮም የላቲን ትርጉም፣ እና ከሁለቱ የዕብራይስጥ ኤምኤምኤስ (ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ 221)። እነርሱ የሚገምቱት ሥሩ כָּרָה እንደሆነ ነው፣ ቢዲቢ 501፣ ኬቢ 497፣ ነገር ግን ለእርሱ የብኪ ምሳሌዎች የሉትም።
4. የተሻለ ሙያዊ ማስታወሻ ግሊሰን መልጎቅ የመጽሐፍ ቅዱስ አስቸጋሪ ነገሮች ኢንሳይክሎፒድያ ተመልከት፣ ገጽ 37 ላይ።

ይህ የመወጋት ሐሳብ ዘወትር የሚያመለክተው ለከፋ ሞት የሚዳርገውን በሰይፍ ወይም በጦር በውጊያ ላይ መወጋትን ነው (በርካታ የተለያዩ ሥሮች፣ ግን ሁለት ትንቢታዊ ጠቀሜታዎች)።

1. ዘካ. 12፡10 – ቢዲቢ 201፣ ኬቢ 230 (ዮሐንስ 19:37፤ ራዕ. 1:7)
2. ኢሳ. 53:5 – ቢዲቢ 319፣ ኬቢ 320

አሻሚነቱ (ማለትም፣ ያልፎ አልፎነቱ፣ በብኪ እዚህጋ ብቻ መሆኑ) የዚህ ቃል፣ በብኪ መልኩ እና በአኪ መልኩ እንዲሠራ አስችሎታል። ይህ መዝሙር በራሱ ጊዜ ፍች ሊኖረው ይገባል፣ ነገር ግን ከክርስቶስ የተለዋጭነት መሥዋዕትነት ባለፈ የሆኑ ነጥቦች መሆኑ ግልጽ ነው (ማለትም፣ እጆቹንና እግሮቹን በችንካር ቸነከሩት)። የአብዛኞቹ የብኪ ጽሑፎች ሙሉ ፍችዎች ወደ ብርሃን የሚመጡት በክርስቶስ ብቻ ነው (ማለትም፣ ዐቢይ ምድብ ወይም ቀጥተኛ ትንበያ)። እኔ እንደማስበው ኢየሱስ ራሱ ነው እነዚህን ጽሑፎች ስለ መከራው እና ትንሣኤው ያመላከተው፣ ለሁለቱ ለኢማሆስ መንገደኞች (ሉቃስ 24፡13-43) እነርሱም በባለ ደርቡ ቤት ለነበሩት የተናገሩት። ከዚያም በኋላ እሱ ተከሰተላቸው እና እጆቹንና እግሮቹን አሳያቸው (ሉቃስ 24፡36-43)።

**22፡14-15፣17** እነዚህ ቁጥሮች የሚገልጹት መከራን/ጥቃትን የሚቀበል ደራሲ የሚሰማውን ነው።

1. እንደ ውኃ ፈሰስኩ

2. አጥንቶቼ ሁሉ ተለያዩ (ማለትም፣ ይህም አንደኛው የስቅለት ውጤት ነው)
3. ልቤ እንደ ሰም ሆነ
4. ኃይሌ (ወይም "ጉሮሮዬ") ደረቀ (ይህ ሊዛመድ የሚችለው ኢየሱስ ከመጨረሻ ቃላቱ በፊት የወሰደውን ሆምጣጤ ነው፣ ማቴ. 27:48፤ ማርቆስ 15:36፤ ዮሐንስ 19:29)

ቁ. 17 ከቁ. 14ለ ጋር እንዴት ወይም ይዛመድ እንደሁ ርግጠኝነት የለም። እያየን ያለነው ከዕብራይስጥ ቅኔ ትይዩነት ጋር ነው! ይህ ዝርው (ስድ ንባብ) እንዳልሆነ አስታውሱ። ይህ ዘይቤአዊ ቋንቋ ነው። ዝርዝሮችን ለሥነ-መለኮታዊ ዓላማ ከመግፋት ተጠንቀቁ፣ በተመስጧዊው የአኪ ደራሲ እስካልተሠራ ድረስ!

**22፡16 "የክፉተኞች ጉባኤ"** "ጉባኤ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 417) ፍችው ስብስብ ወይም ማኅበር ነው። የተለየ ቃል ጥቅም ላይ ውሏል (ቢዲቢ 874) ተመሳሳይ ለሆነ ጽንሰ-ሐሳብ፣ ቁ. 22 እና 25 ላይ። በእነዚህ ሁለት ጉባኤዎች መካከል እንዴት ዓይነቱ ተቃርኖ አለ።
1. ክፉ ሰዎች ለክፉ ዓላማ አንድ ላይ ይሰባሰባሉ
2. መልካም ሰዎች ለምስክርነትና ለአምልኮ ዓላማ ይሰበሰባሉ (መዝ. 1፡5)

የየትኛው ቡድን አባል ለመሆን ትሻለህ?

**22፡18** በብኪ ይህ ሊያመለክት የሚችለው የጦርነት ሰለባን ነው፣ ለድል አድራጊዎች የሚከፋፈል! ምንም ትይዩ የብኪ ምንባብ አለመኖሩን ተገንዘብ። በአኪ እሱ የሚያመለክተው የሮሜ ወታደሮች፣ እነርሱም ስቅላቱን የፈጸሙት የወንጀለኛውን ንብረት ይከፋፈሉ ዘንድ ተፈቅዶላቸዋል፣ እንደ ትርፍ ሥራ ክፍያ።

**መዝሙር ፡ 22፡19-21**

**[19]አንተ ግን፥ አቤቱ፥ ከእኔ አትራቅ**
**አንተ ጉልበቴ፥ እኔን ለመርዳት ፍጠን።**
**[20]ነፍሴን ከሰይፍ አድናት፥**
**ብቻነቴንም ከውሾች እጅ።**
**[21]ከአንበሳ አፍ አድነኝ፥**
**ብቻነቴንም አንድ ቀንድ ካላቸው።**

**22፡19-21** ቁጥር 19 ከቁጥር 11 ጋር ይያያዛል። ተጽዕኗዊው (ከታች ያለውን ማስታወሻ ተመልከት) በሦስት ተተኳሪ ጥያቄዎች ይከተላል።
1. እኔን ለመርዳት ፍጠን – ቢዲቢ 301፣ ኬቢ 300፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 38:22፤ 40:13፤ 70:1፣5፤ 71:12፤ 141:1
2. ነፍሴን አድናት – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
3. አድነኝ – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

ይህ አንጓ የሚዘጋው "መልስልኝ" በሚል ነው፣ በ *ቃል* የተጠናቀቀ ግሥ (ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851) የሚያመለክተውም መዝሙረኛው ወደ ቁርጠኝነት መምጣቱን ነው፣ ያህዌ እንደሚመልስለት (መዝ. 34:4፤ 118:5፤ 120:1)።

መዝሙረኛው እንዴት ጠላቶቹን እንደ ሳለ ተመልከት።
1. ሰይፍ (ማለትም፣ "መውጋት" ምናልባትም በውሻ መነከስ ሊሆን ይችላል፣ ዝከ. ቁ. 16)
2. የውሾች ጥፍር (መዳፍ) (ዝከ. ቁ. 16)
3. የአንበሶች አፍ (ዝከ. ቁ. 13፤ 35:17)
4. የዱር በሬ ቀንዶች (የኃይል ተምሳሌት፣ ኢዮብ 39:9-10)

**22፡19 "አትራቅ"** 22፡11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**22፡20 "ከሰይፍ"** መዝሙረኛው ምን ዓይነት ችግር/መከራ/ጠላቶች በትክክል እንደገጠመው ለማወቅ አዳጋች ነው።
1. *ሕመም*
2. *ዓመጻ*
3. *ወረራ*

ከኢየሱስ ሕይወት ጋር በብዛት ከመያያዙ የተነሣ፣ እኔ የሚመስለኝ "ሰይፍ" ዘይቤአዊ ቋንቋ ነው (መዝ. 37:12-15)።

**መዝሙር ፡ 22፡22-24**

**[22]ስምህን ለወንድሞቼ እነግራቸዋለሁ፥**
**በጉባኤም መካከል አመሰግንሃለሁ።**
**[23]እግዚአብሔርን የምትፈሩ፥ አመስግኑት**
**የያዕቆብ ዘር ሁላችሁ፥ አክብሩት፥**

**የእስራኤልም ዘር ሁላችሁ፥ ፍሩት።**
**[24]የችግረኛን ችግር አልናቀምና፥ ቸልም አላለምና**
**ፊቱንም ከእኔ አልሰወረምና፥**
**ነገር ግን ወደ እርሱ በጮኽሁ ጊዜ ሰማኝ።**

**22፡22-24** ይህ አንጓ ከቁ. 25-31 ጋር ይደራረባል። ሁለቱም የሚናገሩት ስለ ምስክርነት እና ያህዌን ስለ ማመስገን ነው፣ በአምልኮ መቼት (ማለትም፣ ጉባኤ፣ ቁ. 22፤ ታላቅ ጉባኤ፣ ቁ. 25)። ልዩነቱ የዕርዳታው መጠን ነው።

1. ቁ. 22-24 — ጥቃት የደረሰበት
2. ቁ. 25-31 — ዓለም

**22፡22** ሁለት ኅብራዊ ግሦች አሉ።

1. እናገራለሁ – ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765፣ *ፒኤል* ተጓዳኝ
2. አመሰግናለሁ – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ *ፒኤል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

**22፡23** ትይዩውን አስተውል።

1. እናንተ ጌታን የምትፈሩ
2. እናንተ የያዕቆብ ዘሮች (ዘር)
3. የእስራኤል ዘሮች

እነርሱም የሚያደርጉት

1. እንዲያመሰግኑት — ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ *ፒኤል* ተተኳሪ
2. እንዲያከብሩት – ቢዲቢ 457፣ ኬቢ 455፣ *ፒኤል* ተተኳሪ
3. በፊቱ በፍርሃት እንዲቆሙ – ቢዲቢ 158፣ ኬቢ 185፣ *ቃል* ተተኳሪ

**22፡24** ያህዌን ለማመስገን፣ ለማክበር፣ እና ለመፍራት ምክንያቶቹ

1. እሱ አይንቅም (ቢዲቢ 102፣ ኬቢ 117፣ *ቃል* PERFECT) የተጠቃውን
2. እሱ አይጸየፍም (ቢዲቢ 1055፣ ኬቢ 1646፣ *ፒኤል* PERFECT) የተጠቃውን
3. እሱ ፊቱን አይመልስም (ቢዲቢ 711፣ ኬቢ 771፣ *ሂፊል* PERFECT) ከተጠቃው
4. የተጠቃው ለዕርዳታ ሲጮኽ፣ ይሰማል (ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል* PERFECT)

መዝሙረኛው አሁን ተሰምቶታል፣ ያህዌ ሰምቶታል፣ የዕርዳታ ጩኸቱን፣ እና ምላሽ ይሰጠዋል (ዝኪ. ቁ. 21፤22-24)። ይህ የቁ. 1-2፣ 8፣11፣19 የተገላቢጦሽ ነው።

***መዝሙር* ፡ 22፡25-31**

**[25]በታላቅ ጉባኤ ምስጋናዬ ከአንተ ዘንድ ነው።**
**እርሱን በሚፈሩት ፊት ስእለቴን እሰጣለሁ።**
**[26]ችግረኞች ይበላሉ፥ ይጠግቡማል**
**እግዚአብሔርንም የሚሹት ያመሰግኑታል**
**ልባቸውም ለዘላለም ሕያው ይሆናል።**
**[27]የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ያስቡ፥ ወደ እግዚአብሔርም ይመለሱ**
**የአሕዛብ ነገዶች ሁሉ በፊቱ ይሰግዳሉ።**
**[28]መንግሥት ለእግዚአብሔር ነውና፥**
**እርሱም አሕዛብን ይገዛል።**
**[29]የምድር ደንዳኖች ሁሉ ይበላሉ ይሰግዳሉም**
**ወደ መሬት የሚወርዱት ሁሉ በፊቱ ይንበረከካሉ**
**ነፍሴም ስለ እርሱ በሕይወት ትኖራለች።**
**[30]ዘሬ ይገዛለታል**
**የምትመጣው ትውልድ ለእግዚአብሔር ትነግረዋለች**
**[31]ጽድቁንም ለሚወለደው ሕዝብ፥**
**እግዚአብሔር ያደረገውን ጽድቁን፥ ይነግራሉ።**

**22፡25-26** መቼቱ የአምልኮ መቼት ነው፣ ምናልባትም የማደርያ ድንኳን/መቅደስ (ማለትም፣ "መሐላን መፈጸም" እና "በልቶ መጥገብ")። አምላኪዎቹ እንደ "ተጠቁት" ነው የተወሰዱት (ቢዲቢ 776) ከቁ. 24። እነርሱም የሚሆኑት

1. ያህዌን የሚፈልጉ፣ ቁ. 26 – ቢዲቢ 205፣ ኬቢ 233፣ *ቃል* አንቀጽ
2. ያህዌን የሚያመሰግኑ፣ ቁ. 26 – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ *ፒኤል* ያልተጠናቀቀ

**22:26 “ልባቸውም ለዘላለም ሕያው ይሆናል”** ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ *ቃል ተጽዕኗዊ*) የሚያንጸባርቀው የተለመደውን ፈሊጥ ነው፣ ለእስራኤል/ይሁዳ ነገሥታት ጥቅም ላይ የዋለ። መዝሙረኛው ንጉሥ ነው። የመለዋወጥ ነገር ያለ ይመስላል፣ በቁ. 28-31፣ በኪዳኑ አምላክ እና በእርሱ ንጉሣዊ ተወካዩ መካከል (ማለትም፣ መሢሕ፣ 2 ሳሙ. 7:1-17)።

**22፡27** ሁለንተናዊ አጽንዖቱ የሚያስፈራና ስሕተት የሌለበት ነው።

1. የምድር ዳርቻዎች ሁሉ (ኢሳ. 45:22፤ 49:6፤ 52:10፤ 66:23፤ ኤር. 16:19፤ ሚኪያስ 5:4)
2. የአሕዛብ ወገኖች (ዘፍ. 12:3፤ ሐዋ3:25፤ ገላ. 3:8)

አሕዛብ ምን እንደሚያደርጉ ተገንዘቡ።

1. ያህዌን ያስታውሳሉ – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
2. ወደ ያህዌ ይመለሳሉ – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ (ይህ *ግሥ* ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለንስሐ ነው)
3. በፊትህ/በፊቱ ይሰግዳሉ – ቢዲቢ 1005፣ ኬቢ 295፣ *ሂሽታፌል/ሂዝፋሌል*፣ መዝ. 66:4፤ 86:9

**22፡28** የሁለንተናዊው አጽንዖት ምክንያት ተሰጥቷል። ይህ ዘወትር የያህዌ ፍላጎት ነው። እሱም የዘፍ. 1፡26-27 ግልጽ አንድምታ ነው፣ እንዲሁም የአሀዳዊነት ሥነ-መለኮታዊ ማስረገጫ!

1. የያህዌ መንግሥት (መዝ. 47:7-9፤ 67:4፤ አብድ. ቁ. 21፤ ዘካ. 14:9)
2. እሱም አሕዛብን ይገዛል (መዝ. 47:8፤ 1 ዜና. 16:31)

**22፡29** ይህ ቁጥር ለመተርጎም አስቸጋሪ ነው። በጥሬው ሊሆን የሚችለው

“በሙሉ ኃይላቸው የሆኑት ሁሉ ተመግበው በፊቱ ይሰግዳሉ፤
ወደ መሬት የሚወርዱት ሁሉ በፊቱ ይሰግዳሉ” (ጄፒኤስኦኤ)

ግልጽ የሆነ ተቃርኖ አለ፣ በሀብታም እና ደሀ/የሚሞት መሐከል። የቁጥሩ ፍሬ-ሐሳብ ማንም ይሁን፣ የትም ስፍራ ያህዌን/መሢሑን ያመልካል ነው። ከዚህ በላይ መጓዝ እንችላለን፣ ይህ ቁጥር ስለ ከሕይወት በኋላ ማስተማሩን ለመመልከት? በአኪ ይህን መዝሙር ከመጠቀም አኳያ፣ የኢየሱስን ሞት እንደሚያመለክት፣ ሊሆን ይችላል (ሉቃስ 23፡39-43)።

አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ቁ. 29ለ ከፊሊ. 2፡10 ጋር አንዳች ግንኙነት ካለው። አኪ ያስረግጣል፣ አንድ ቀን ጉልበት ሁሉ እንደሚንበረከክ።

1. የጠፉት
2. የዳኑት

ይህ በፍርድ ላይ መንበርከክ ለሚጠፉት የእምነት ድርጊት አይደለም፣ ነገር ግን ለፍትሐዊ ፍርድ እውቅና መስጠት እንጂ።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **“ነፍሱን በሕይወት ማቆየት የማይችለው እንኳ”** |
| **አየተመት** | **“እኔ ለእርሱ እኖራለሁ”** |
| **አኢመቅ** | **“የሞቱት እነርሱ”** |
| **የተእመቅ** | **“እኔ ግን በእርሱ ሳቢያ እኖራለሁ”** |

ኤምቲ በአአመመቅ ተንጸባርቋል፣ ማለትም የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት “ሐ” ደረጃ ይሰጠዋል (ምክንያታዊ ጥርጣሬ)። LXX በአየተመት ተንጸባርቋል፣ ይኸውም የሁለት ተናባቢዎችን ማሻሻል ያካተተ።

ኤምቲ –ונפשׁחיהאלו

LXX – ונפשׁחיהלוי

**22:30-31** የአዲስ እምነት ዘር/ቤተሰብ/ዘር ይመጣል፣ ከከፋው የመከራ ሁነት። እነርሱም መከራ የተቀበለውን ያገለግሉታል፣ ጻድቅነቱንም ያውጃሉ (ማለትም፣ ንጽሕና)!

**22:**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“እሱም አደረገው”** |
| **አኪጀት** | **“እሱ ይህን አደረገ”** |
| **አየተመት** | **“እሱ አደረገው”** |
| **አእቅ** | **“እግዚአብሔር ሕዝቡን አዳነ”** |
| **አኢመቅ** | **“እሱም ፈጸመው”** |
| **LXX፣ ጄፒኤስኦኤ፣** | |
| **የተእመቅ** | **“እግዚአብሔር አደረገ”** |

*ግሥ* (ቢዲቢ 793፣ ኬቢ 889፣ *ቃል* PERFECT) የሚናገረው ስለ ተከናወነ ተግባር ነው (1 ሳሙ.26:25፤ ዳን. 8:24)። ከአኪ አጠቃቀም አኳያ ይህ የሚያመለክተው ስለ ሰው ልጅ መዋጀት ነው፣ በቀራንዮ (ሮሜ. 5:12-21)፣ ማስረጃና ማረጋገጫ ሆኗል በባዶ መቃብር (1 ቆሮ. 15:1-28)!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ትንበያ፣ ዐቢይ ምድብ ወይስ ባለ ብዙ ፍጻሜ ትንቢት?
2. በዚህ መዝሙርና በኢየሱስ ሞት መካከል ያለውን ታሳቢ ግንኙነት ዘርዝር?
3. መዝሙረኛው ጠላቶቹን በበርካታ እንስሶች ስም ጠርቷቸዋል። ዘርዝራቸው።
4. "የተወጋው" በሚለው ቃል፣ ቁ. 16 ላይ ጥርጣሬ ያለው ለምንድነው?
5. ቁጥር 22 ላይ ያለውን የሁኔታ ለውጥ ግለጽ።
6. ቁጥር 27-29 ከሥነ-መለኮት አኳያ እጅግ ጠቃሚ የሆኑት ለምንድነው?

## መዝሙር 23
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ፣ የመዝሙረኛው እረኛ<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>(የዳዊት መዝሙር) | ጌታ የሕዝቡ እረኛ | በእግዚአብሔር ጥበቃ የመታመን መግለጫ (የእምነት መዝሙር) | ጌታ እረኛችን | መልካሙ እረኛ |
| 23:1-3 | 23:1-3 | 23:1-3 | 23:1-4 | 23:1-2ሀ<br>23:2ለ-3 |
| 23:4-6 | 23:4 | 23:4 | | 23:4 |
| | 23:5-6 | 23:5-6 | 23:5-6 | 23:5<br>23:6 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ እጅግ የታወቀው ምንባብ ነው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ፣ በአጠቃላዩ ሰው፤ ሌለኞቹም ዮሐንስ 3፡16 ወይም "የፍቅር ምዕራፍ" 1 ቆሮንቶስ 13።
ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ ርዕዮተ-ዓለም ነው፣ የታማኝ ተከታይ። አትኩሮቱ በያህዌ እና በእርሱ መገኘት፣ ክብካቤና ሰጭነት ላይ ነው!

ለ. እሱ ሦስት የተለያዩ ባህላዊ ዘይቤዎች ይጠቀማል፣ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነትን ግለሰባዊ ገጽታን ቀረቤታ ለመግለጽ (ማለትም፣ "እኔ፣" "እኔን፣" "የእኔ")።
1. እግዚአብሔር እንደ እረኛ፤ የእርሱ ሕዝቦችም እንደ ችግረኛ በጎች፣ መዝ. 23፡1-2
2. እግዚአብሔር እንደ መሪ፤ የእርሱ ሕዝቦችም እንደ ችግረኛ መናኞች፣ ቁ. 3-4
3. እግዚአብሔር እንደ ጋባዥ፤ የእርሱ ሕዝቦችም እንደ ተጋባዥ እንግዶች፣ ቁ. 5-6

ሐ. ይህ መዝሙር አስር ያልተጠናቀቁ አሉት (በሂደት ላይ ያሉ ድርጊቶች) ግሦች። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ይኖራል፣ በቀውስ ጊዜያት ብቻ ሳይሆን። ይህ የብኪ አንጻራዊ ነጥብ ነው፣ የማቴ. 6፡11።
1. አላጣም — ቢዲቢ 341፣ ኬቢ 338፣ አሉታዊ ያልተጠናቀቀ መዝ. 34፡9፣10
2. ያሳርፈኛል – ቢዲቢ 918፣ ኬቢ 1181፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ
3. ይመራኛል – ቢዲቢ 624፣ ኬቢ 675፣ *ፒይል* ያልተጠናቀቀ

4. ነፍሴን መለሳት – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ ፖለል ያልተጠናቀቀ መዝ. 19:7
5. ይመራኛል – ቢዲቢ 634፣ ኬቢ 685፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 5:8፤ 31:3
6. ባልፍ እንኳ – ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ ያልተጠናቀቀ
7. ክፉን አልፈራም – ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ ያልተጠናቀቀ መዝ. 27:1
8. እነርሱ (ማለትም፣ በትርና ምርኩዝ) ያጸናኑኛል – ቢዲቢ 636፣ ኬቢ 688፣ ፒይል ያልተጠናቀቀ
9. በፊቴም ማዕድ አዘጋጀኽልኝ – ቢዲቢ 789፣ ኬቢ 884፣ ያልተጠናቀቀ
10. ቸርነትህና ምሕረትህ ይከተሉኛል – ቢዲቢ 922፣ ኬቢ 1191፣ ያልተጠናቀቀ
11. እኖራለሁ/ዐርፋለሁ – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ የተጠናቀቀ ከዋው፣ መዝ. 27:4-6

መ. የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 230) እንደመዘገበው ይህ መዝሙር ተመሳሳይ አቻ የለውም። የቅኔ ስንኞቹ ምጣኔ የላቸውም (ማለትም፣ ተመሳሳይ ቁመት)። እሱ የማጠቃለያ ቃል ጡዘታዊ ጫፍ ነው። አጭርነቱ የመልእክቱን አጽንዖትና ኃይል ያጎላል!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 23፡1-3**

**[1]እግዚአብሔር እረኛዬ ነው፥**
**የሚያሳጣኝም የለም።**
**[2]በለመለመ መስክ ያሳድረኛል**
**በዕረፍት ውኃ ዘንድ ይመራኛል።**
**[3]ነፍሴን መለሳት፥**
**ስለ ስሙም**
**በጽድቅ መንገድ መራኝ።**

**23፡1** የመክፈቻው ስንኝ በጥሬው "እረኛዬ ያህዌ ነው" የሚል ነው። ብቸኛው ግሣዊ የድርጊት አንቀጽ ነው (ቢዲቢ 944፣ ኬቢ 1258)። ያህዌ እንደ እረኛ የሆነበት ጽንሰ-ሐሳብ ንጉሣዊ መጠሪያ ነበር፣ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) (ማለትም፣ ሐሙራቢ)። በብኪ እሱ ጥቅም ላይ የሚውልበት ስሜት

1. ለመግለጫ – መዝ. 78:52፤ ሕዝ. 34:11-13
2. የኪዳን ስም – መዝ. 80:1
3. ዘይቤ – ኢሳ. 40:11፤ ኤር. 31:10
4. መሢሑ እንደ እረኛ – ዮሐንስ 10:11፤ 1 ጴጥ. 2:25

እሱም ኃይለኛ ምናባዊ ነው፣ ምክንያቱም

1. የቀረበና ቋሚነት ያለው መገኘት፣ እረኛው ከበጎቹ ጋር
2. በጎች ስለሚያስፈልጋቸው፣ ሁልጊዜ የሚኖር፣ ተንከባካቢ እና ጠባቂ

▣ **"የሚያሳጣኝ የለም"** ይህ ቀላል ግን አጠቃላይ ሐረግ ነው። እሱም እያንዳንዱን መሻት ወይም ፍላጎት ሊጠቅስ አይችልም። እሱ የሚጠቅሰው ለበጎች የሚያስፈልገው መልካም የሆነው ነው። እግዚአብሔር ለወደቁት ሰዎች ሊያደርግ የሚችለው የከፋ ነገር ለራስ-ወዳድ፣ ዓለማዊ ጥያቄአቸው አዎንታዊ ምላሽ መስጠት ነው። የነፍሳችን እረኛ ለእኛ እጅግ መልካም የሆነውን ያደርግልናል ይሰጠናልም!

**23፡2** ይህ ቁጥር፣ ቁጥር 1ን የሚገልጽ ነው። እረኛው ያውቃል፣ በጎች የሚያስፈልጋቸውን

1. ዕረፍት
2. ምግብ
3. ውኃ

እሱም እነዚህን ይሰጣል፣ በጎች ሊቀበሉበት በሚችሉት መንገዶች (ማለትም፣ ተገቢ ምግብ፣ ውኃ በቀላሉ እንዲጠጡ)። ብቻችንን አይደለንም (መዝሙር 139)! በሕይወታችን ዓላማ አለ፣ በወደቀው ዓለም እንኳ ቢሆን። ይህ ማለት ግን ሥቃይ-የለሽ፣ ችግር-የለሽ የሕይወት ልምምዶች ይሆናል የሚል አንድምታ የለውም። እሱ የሚያስረግጠው እሱ ከእኛ ጋር፣ እና ለእኛ መሆኑን ነው (1 ቆሮ. 10፡ 13)።

**23፡3 "ነፍሴን መለሳት"** ይህ ቁጥር የወደቀውን የሰው ልጅ ሁኔታ የሚያጠቃልልና እውቅና የሚሰጥ ነው (ኢሳ. 53፡6)። "መመለስ" እንፈልጋለን። ይህ ግሥ (ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427) ሁነኛው ግሥ ነው፣ ስለ "ንስሐ" ጥቅም ላይ የዋለ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት 7፡12። ይኸው ተመሳሳይ ግሥ ቁ. 6 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ወደ ማደሪያው ድንኳን/መቅደስ ስለ መመለስ፣ ለሕይወት ዘመን ኅብረት። ታማኝ ተከታዮች፣ በእግዚአብሔር መንፈስ የተነቃቁ፣ ከግለኝነትና ከኃጢአት መመለስ ይኖርባቸዋል፣ ወደ እግዚአብሔር። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ደኅንነት

1. ከውድቀት መመለስ
2. ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረት መመለስ
3. ከሚታወቅ ኃጢአት መመለስ እና ለማይታወቅ ኃጢአት ይቅርታ (መዝ. 19፡12-14)
4. ወደ እግዚአብሔር በዓላማ መመለስ (ማለትም፣ በኅብረት፣ በመታዘዝ፣ እና በአምልኮ፣ ዝከ. 23፡3ለ)

"ነፍስ" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል *ኔፊሽ* (ቢ.ዲ.ቢ. 659፣ ኬ.ቢ. 711፣ ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 3፡2 ላይ) ሊያመለክት የሚችለውም

1. የሰው ልጆችን — ዘፍ. 2፡7
2. እንስሳት — ዘፍ. 1፡24፤ 2፡19

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"በጽድቅ መንገድ"**
**አየተመት፣ አእቅ፣**
**ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ** **"በቀና መንገድ"**
**አኢመቅ** **"ፍርድ ባለበት መንገድ"**

ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ይህ የሚያመለክተው አስተማማኝ መንገዶችን ነው፣ ወደ ምግብና ውኃ የሚያመራ። "ቀና" ወይም "የጽድቅ" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 841፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡5 ላይ) በመሠረቱ እሱ ሥነ-ምግባራዊ፣ ሞራላዊ ገጽታ አለው፣ እናም በርግጥ እዚህጋ ያመለክታል (ኤፌ. 1፡4፤ 2፡10)። እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት በመታዘዝ መኖር ነው፣ ለተገለጠው ፍቃዱ። ይህ አንድምታ ዳግም ተጠናክሯል፣ በቁ. 3 የመጨረሻው ሐረግ፣ "ስለ ስሙ ሲል" (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡11-12 ላይ)። እሱ "ይመራል"፣ ስለዚህ ለእርሱ ነው "የምንኖረው።" እኛ እንደ ታማኝ ተከታዮች እሱን እንገልጣለን! እሱ እኛን አድኖናል፣ ሌሎችን ለማዳን። የዳንነው ለማገልገል ነው!

"ስለ ስሙ ሲል፣" ለሚለው ሐረግ መዝ. 25፡11፤ 31፡3፤ 79፡9፤ 106፡8፤ 109፡21፤ 143፡11 ተመልከት። የምንኖረው የእርሱን ባሕርይና ዓላማ ለመግለጥ ነው። እስራኤል ዘወትር አላደረገውም (ኤር. 14፡21፤ ሕዝ. 20፡9፣14፣22፤ 36፡22-38)።

**መዝሙር ፡ 23፡4-6**

**4በሞት ጥላ መካከል እንኳ ብሄድ**
**አንተ ከእኔ ጋር ነህና ክፉን አልፈራም**
**በትርህና ምርኵዝህ እነርሱ ያጽናኑኛል።**
**5በፊቴ ገበታን አዘጋጀህልኝ በጠላቶቼ ፊት ለፊት**
**ራሴን በዘይት ቀባህ፥**
**ጽዋዬም የተረፈ ነው።**
**6ቸርነትህና ምሕረትህ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ ይከተሉኛል፥**
**በእግዚአብሔርም ቤት ለዘላለም እኖራለሁ።**

**23፡4**

**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"በሞት ጥላ ሸለቆ"**
**አየተመት** **"በጨለማ ሸለቆ"**
**አእቅ** **"በጥልቁ ጨለማ"**
**አኢመቅ** **"እንደ ሞት በጨለመ ሸለቆ"**
**LXX** **"የሞት ጥላ"**
**ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ** **"የጥልቁ ጨለማ ሸለቆ"**

ይህ አወቃቀሩ የ "ሸለቆ" (ቢ.ዲ.ቢ. 161) እና "ጨለማ፣" "ጥልቅ ጥላ" ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 853)። ብዙዎቹ ሊቃውንት የሚያስቡት צלמות ከ צל እና מות መምጣቱን ነው።

1. ጥላ፣ጨፍጋጋ፣ ጨለማ – ቢ.ዲ.ቢ. 853፣ ኬ.ቢ. 1024
2. ሞት፣ መሞት – ቢ.ዲ.ቢ. 560፣ ኬ.ቢ. 563

እሱም አስራ ስምንት ጊዜ በብኪ ጥቅም ላይ ውሏል (አስር ጊዜ ኢዮብ ላይ) ለ

1. ሞት – ኢዮብ 10፡21፣22፤ 38፡17፤ መዝ. 107፡10፣14
2. መከራ – ኢዮብ 16፡16፤ 24፡17፤ መዝ. 44፡20
3. ዘወትርም በዐውደ-ጽሑፍ ከብርሃን ተጻራሪ – ኢዮብ 3፡5፤ 12፡22፤ 24፡17፤ 28፡3፤ 34፡22፤ ኤር. 13፡16፤ አሞጽ 5፡8

እሱም በተምሳሌታዊነት ለአስፈሪ፣ አስጨናቂ፣ እና የሞት ልምምዶች ጥቅም ላይ ውሏል፣ ለወደቀው ሰው፣ በዚህ በወደቀው ዓለም። ሕይወት አስፈሪ ነው፣ እግዚአብሔር ግን ከእኛ ጋር አለ (ዝከ. 23፡4ለ፣ሐ፤ ዘዳ. 31፡6፣8፤ ማቴ. 28፡20፤ 2 ቆሮ. 4፡9፤ ዕብ. 13፡5)።

▣ **"ፍርሃት... ማጽናናት"** እንዴት ያለው ተቃርኖ ነው! የታመኑት መከራ ይገጥማቸዋል፣ በመተማመን፣ እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር በመሆኑ ምክንያት (ማለትም፣ ከእረኛው በትርና ምርኩዝ ጋር ተምሳሌታዊ የሆነ፣ የእርሱ የክብካቤና የጥበቃ መሣርያዎች)።

ችግሮች ይመጣሉ! ፈጽሞ ብቻችንን አንጋፈጣቸውም! ፈጽሞ! እሱ ፈጽሞ አይለቀንም ወይም አይተወንም (ዘዳ. 31:6፤ ኢያ. 1:5፤ ዕብ. 13:5)።

**23፡5** እግዚአብሔር ከእኛ እና ለእኛ መሆኑ ብቻ አይደለም፣ እሱ ይከላከልልናል፣ ሊጎዱን ባሉት ፊት። ባህላዊው እንግዳ ተቀባይነት ለተትረፈረፈው የእግዚአብሔር ፍቅር ማሳያ ጥቅም ላይ ውሏል።

1. ገበታ ማዘጋጀት
2. ራስ መቀባት
3. የተትረፈረፈ ፍቅር

▣ **"የተትረፈረፈ"** ይህ ያልፎ አልፎ ቃል ነው (ቢዲቢ 924፣ "የሞላ") እዚህጋ ብቻ ነው በብኪ የሚገኘው። መዝሙር 66፡12 "የተትረፈረፈ ስፍራ" የሚል አለው (በመጠኑ የተለየ ፊደል)። LXX እሱን የሚተረጉመው "ጽዋህ ያስደስተኛል፣ እንደ መልካም ወይን" ወይም "ጽዋህ እጅግ ያስደስታል" በሚል ነው። እሱም ሐሳቡን ከ "ሞላ" በግልጽ የወሰደ፣ እንደ "መደሰት።"

**23፡6** **"ቸርነት"** ግሥ (ቢዲቢ 373)፣ ቅጽል (ቢዲቢ 373 II)፣ እና ስም (ቢዲቢ 375III) ሁሉም የሚገልጹት "መልካም፣" "የሚያስደስት፣" "የሚጠቅመውን" ነው። እነሱም መዝሙር፣ ምሳሌ፣ እና መክብብ ላይ በብዛት ጥቅም ላይ ውለዋል። እግዚአብሔር ለኪዳኑ ሕዝቦች ሊያደርግ የሚሻው ይህንን ነው (ማለትም፣ ዘዳ. 30፡9፤15)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ቸርነት"** |
| **አኪጀት፣ አየተመት** | **"ምሕረት"** |
| **አእቅ** | **"ፍቅር"** |
| **አኢመቅ** | **"የታመነ ፍቅር"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"አስደናቂ ፍቅር"** |
| **የተእመቅ** | **"የማይወድቅ ፍቅር"** |

ይህ ልዩ ኪዳን ነው፣ ስም ሄሰድ (ቢዲቢ 338)፣ እሱም የሚገልጸው የያህዌን የታመነ፣ የማይገባን፣ የኪዳን ታማኝነት ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7 ላይ)። የኪዳን ታማኝነት በሞላ እጅግ አስደናቂ ነው፣ ከእስራኤል አለመታዘዝ አኳያ (ነህ. 9፡6-38)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት፣ አየተመት፣ የተእመቅ** | **"መከተል"** |
| **አእቅ** | **"ከእኔ ጋር ይሆናሉ"** |
| **አኢመቅ፣ LXX፣ ጀፒኤስኦኤ** | **"መከተል"** |

ይህ ግሥ (ቢዲቢ 922፣ ኬቢ 1191፣ ያልተጠናቀቀ) ከ "መከተል" እጅግ የበረታ ስሜት አለው። እሱ የሚጠቅሰው ንቁ ዲጋፊ ድርጊትን ነው። እስቲ አስቡ፣ የእግዚአብሔር የኪዳን ፍቅር እስራኤላውያንን ሲያሳድድ። እሱ የሚሆነው

1. ወታደራዊ ቃል
2. የአደን ቃል
3. የፍርድ ቃል

ቁም! ወደ ኋላ ዞር! ማን እንደሚያሳድድህ ተመልከት፣ አዎ አንተ!

▣ በዚህ የብኪ ዐውደ-ጽሑፍ የመጨረሻው ስንኝ የዘላለም ሕይወትን የሚጠቅስ አይደለም (ሌሎች ጽሑፎን ይጠቅሳሉ፣ ራዕ. 21:3-7፤ 22:1-5) ነገር ግን የኪዳን መልካምነትን ሕይወት (ዘዳ. 30፡3፤15፤19)። ይህም በየዕለቱ ሕይወት የምንኖረው ነው፣ እና መደበኛ የማደሪያው ድንኳን/መቅደስ አምልኮ።

ግሥ (ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ የተጠናቀቀ ከዋው ጋር) ሊጠቀስ የሚችለው

1. አብሮ መቀመጥ (የጥንቶቹ)
2. መመለስ (ዕብራውያን)

▣ **"ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 9፡5 ላይ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ያህዌ እንዴት እረኛ ይመስላል?
2. ቁጥር 1-3 ያሉት ግሦች በታማኝ ተከታዮች የየዕለቱ ሕይወት እንዴት ተግባራዊ ይደረጋሉ?
3. “የሞት ጥላ ሸለቆ”ን ግለጽ።
4. ይህ መዝሙር ለሕይወት በኋላ ንግር ነውን?
5. መዝሙሩ ለሁሉም ዘመናት አማኞች እጅግ ትርጉም-አዘል የሆነው ለምንድነው?

# መዝሙር 24
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የክብር ንጉሥ ይግባ<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር | የክብር ንጉሥ እና መንግሥቱ | ወደ መቅደስ ስለመግባት ሥርዓት | ታላቁ ንጉሥ | ወደ መቅደስ በክብር ስለመግባት |
| 24:1-6 | 24:1-2 | 24:1-2 | 24:1-2 | 24:1-2 |
| | 24:3-6 | 24:3-6 | 24:3-6 | 24:3 |
| | | | | 24:4 |
| | | | | 24:5-6 |
| 24:7-10 | 24:7-10 | 24:7-10 | 24:7-8 | 24:7 |
| | | | | 24:8 |
| | | | 24:9-10 | 24:9 |
| | | | | 24:10 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር ስለ
1. ያህዌ እንደ ፈጣሪ (ቁ. 1-2) እና ተዋጊ (ቁ. 8)
2. ወደ እርሱ መቅረብ የቻሉ ያመልኩታል (ቁ. 3-6)

ለ. ተመሳሳይ ትይዩዎች በቋሚነት ጥቅም ላይ መዋላቸውን ተገንዘብ

ሐ. ተጠቃሾቹን ስሞች ተገንዘብ
1. እናንት ደጆች፣ ቁ. 7፣9
2. እናንት የጥንት በሮች፣ ቁ. 7፣9
3. ያዕቆብ፣ ቁ. 6 ምናልባት "ያዕቆብ ሆይ" ሊሆን ይችላል

መ. መጠሪያዎቹንና ገላጭ ሐረጎቹን ተገንዘብ
1. የድኅንነቱ አምላክ፣ ቁ. 5 (መዝ. 18:46፤ 25:5፤ 51:14፤ 79:9)
2. የክብር አምላክ፣ ቁ. 7፣8፣10 (ሁለቴ)
3. ያህዌ ብርቱና ኃያል፣ ቁ. 8
4. ያህዌ በሰልፍ ኃያል፣ ቁ.8

5. የሠራዊት ጌታ፣ ቁ. 10
ቁጥር 3፣4፣5 ወታደራዊ ፍች አላቸው።

ሠ. ያህዌን ለማምለክ የተፈቀደላቸውን ተገንዘብ (መዝሙር 15) በማደርያው ድንኳን/መቅደሱ፣ ባሕርያቸው የሆነው
1. እጆቹ ንጹሕ የሆኑ፣ ኢዮብ 17፡9፤ 22፡30
2. ልበ-ንጹሕ የሆነ፣ መዝ. 73፡1
3. ነፍሱን በሐሰት ያላነሣ፣ ሕዝ. 18፡15
4. በሐሰት ያልማለ
5. እነርሱ እሱን የሚፈልጉት፣ መዝ. 9:10፤ 24:4፣8፤ 27:8፤ 34:4፤ 69:32
ይህ የአምልኮ መዝሙር ነበር በሌዋውያን፣ ምዕመናን በበዓል ቀን ሲመጡ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 24፡1-6**

**[1]ምድርና ሞላዋ ለእግዚአብሔር ናት፥**
**ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ሁሉ።**
**[2]እርሱ በባሕሮች መሥርቶአታልና፥**
**በፈሳሾችም አጽንቶአታልና።**
**[3]ወደ እግዚአብሔር ተራራ ማን ይወጣል?**
**በቅድስናውስ ስፍራ ማን ይቆማል?**
**[4]እጆቹ የነጹ፥ ልቡም ንጹሕ የሆነ፥**
**ነፍሱን ለከንቱ ያላነሣ፥**
**ለባልንጀራውም በሽንገላ ያልማለ።**
**[5]እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ በረከትን**
**ከመድኃኒቱ አምላክም ምሕረትን ይቀበላል።**
**[6]ይህች ትውልድ እርሱን የምትፈልግ ናት፥**
**የያዕቆብን አምላክ ፊት የምትፈልግ። ሴላህ**

**24፡1-2** እነዚህ ቁጥሮች ለያህዌ እንደ ፈጣሪ አጽንዖት የሚሰጡ ናቸው (ዘፍጥረት 1-2፤ ዘጸ. 9:29፤ 19:5፤ መዝ. 50:12፤ 89:11፤ መዝሙር 104)፣ ሁለቱንም ሕይወት የሌላቸውን እና ሕይወት ያላቸውን፣ ሁለቱንም እንስሳትንና ሰዎችን (መዝ. 146:6፤ Jer. 27:5፤ 51:15)።

ቁጥር 2 ላይ ምናባዊው ተምሳሌት የሚያሳየው ምድር በውኃ እንደ ተመሠረተች ነው (መዝ. 104:3፣5፤ 136፡6)። ውኃ (ሁለቱም፣ ንጹሕ [ማለትም፣ ወንዞች] እና ጨዋማ [ማለትም፣ ባሕሮች]) በዘፍጥረት 1 ላይ እንደተፈጠሩ አልተባለም። በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አፈ-ታሪክ ውኃ የሚጠቀሰው እንደ ቀውስ አውሬ ነው። ለተጨማሪ መረጃ፡
1. ዘፍ. 1፡2 ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፣ ዘፍጥረት 1-11 ነጻ ዌብ ሳይት ላይ www.freebiblecommentary.org
2. ኒዶቲ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 545-549፣ "መለኮታዊ ተዋጊ")። በመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ውኃን ይቆጣጠራል (አሞጽ 9፡6) እሱ፣ የመራባት ጣዖታት ሳይሆኑ፣ ለራሱ ዓላማ ይጠቀምበታል።
1. ፍጥረት እና ፍርድ
2. ዕጽዋትንና የእንስሳትን ሕይወት ይመግባል (ማለትም፣ ዓመታዊ ዝናብ)

**24፡1 "ምድር... ዓለም"** የመጀመሪያው ቃል (ቢዲቢ 75) እጅግ የተለመደ ነው፣ እናም ሰፊ የፍች መስክ አለው፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡2 ላይ። ሁለተኛው ቃል (ቢዲቢ 385) ቅኔአዊ ተመሳሳይ ነው፣ ባብዛኛው መዝሙር እና ኢሳይያስ ላይ ጥቅም ላይ የዋለ።

**24፡2 "መሠረታት... አጸናት"** እነዚህ ሁለት ግሦች (ምሳ. 3፡19)
1. ቢዲቢ 413፣ ኬቢ 417፣ የተጠናቀቀ
2. ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 414፣ ፖሄል ያልተጠናቀቀ
በትይዩአዊ ግንኙነት ላይ ናቸው። ሁለቱም የሚያስረግጡት ያህዌ፣ ፈጣሪ አምላክ ደረቁን ምድር በጽኑ ምሰሶዎች ላይ መመሥረቱን ነው (1 ሳሙ.2:8፤ ኢዮብ 9:6፤ መዝ . 75:3)፣ እሱም የውቅያኖስ ወለሎችና የተራሮች ሥርጋ የሚደርስ (ኢዮብ 38:4-6፤ መዝ. 18:7፣ 15፤ ዮናስ 2:6)።

ይህ ዘመናዊ ሳይንሳዊ ገለጻ አይደለም፣ ነገር ግን ቅድመ-ሳይንሳዊ ቅኔአዊ ምናባዊ እንጂ! መጽሐፍ ቅዱስ ለዘመናዊው ምዕራባዊ ሳይንስ ምላሽ ለመስጠት ወይም መረጃ ለማቅረብ አልተጻፈም። እሱ ጥንታዊ ቅርብ ምስራቃዊ መጽሐፍ ነው፣ በክስተታዊ ቋንቋ የተጻፈ (ማለትም፣ ነገሮች በአምስቱ ሕዋሳት እንደሚከሰቱ)።

**24፡3-6** ይህ የተለየ አንጓ ሊሆን ይችላል (የእንግሊዝኛ ትርጉም ጽሑፋዊ ምድብ የመጀመሪያውን ገጽ ተመልከት)። እሱም የፍጥረትን አምላክ ለማምለክ የሚፈልጉትን ይገልጻል (ዝኪ. ቁ. 6 እና ዐውደ ጽሑፋዊ ይዘት ሠ)።

እሱ የሚመለክበት ስፍራ የእርሱ ማደሪያ ድንኳን/መቅደስ በኢየሩሳሌም ነው (ቁ. 3)። መቅደስ የሞላው ዓለም ተምሳሌት ነው (የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 1308፣ ቁ. 1-2 እና አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 762፣ ቁ. 2)። አዲስ መጽሐፍ ዘፍጥረት 1-2ን እንድገነዘብ የረዳኝ፣ ያህዌ መቅደሱን እንደገነባ፣ የጆን ዋልተን፣ *የዘፍጥረት አንድ የጠፋው ዓለም ነው።* እንደምትመለከቱት ተስፋ አደርጋለሁ። እሱም ግጭቱን ለመቅረፍ፣ ወይም ቢያንስ ለመቀነስ አቅም አለው

1. የምድር ዕድሜን
2. ዝግመተ-ለውጥን
3. የዘፍጥረት 1-2 ዓላማ
4. ዘፍጥረት ከሌሎቹ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) የፍጥረት ሐተታዎች ጋር እንዴት እንደሚዛመድ

ይሄንን ለማድረግ፣ የኪዳን ታዛዥነት (መዝሙር 15) ያስፈልጋል (ዝኪ. ቁ. 4)። የሚታዘዙት ይቀበላሉ

1. ከያህዌ በረከትን፣ ቁ. 5
2. ጽድቅን (ማለትም፣ መከላከያ፣ ኢሳ. 54፡17) ከደኅንነቱ አምላክ፣ ቁ. 5

ቁጥር 4-6 ሁለቱን ጥያቄዎች ይመልሳሉ፣ ቁጥር 3 ላይ የተመለከቱትን። ይህ አንጓ የከፍታ አምልኮ ሥርዓት ሊሆን ይችላል፣ በሌዋውያን የሚዘመር፣ ምዕመናን ወደ ማደሪያው ድንኳን/መቅደስ ሲወጡ፣ በሞሪያ ተራራ ላይ።

**24፡4 "ማንሣት"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724) በዚህ መዝሙር ላይ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ውሏል።

1. ቁ. 4 — ነፍሱን በከንቱ ያላነሣ (የተጠናቀቀ)
2. ቁ. 5 — ይቀበላል ("ተሸክሞ ይሄዳል") በረከትን (ያልተጠናቀቀ)
3. ቁ. 7፣9 – እናንተ መኳንንቶች፣ በሮችን ከፈቱ (ተተኳሪ)
4. ቁ. 7፣9 — ይከፈቱ፣ የጥንት ደጆች (ተተኳሪ)
5. ዘፍጥረት ከዘመናዊ ሳይንስ ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ወይም እንደማይዛመድ

▣ **"ነፍስ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል *ኔፊሽ* ነው (ቢዲቢ 659)። መዝ. 3፡2 እና 23፡3 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ለሐሰተኝነት"** |
| **አኪጀት** | **"ለጣዖት"** |
| **አየተመት፣ የተእመቅ** | **"ሐሰት ለሆነ"** |
| **አእቅ** | **"ጣዖትን ለማምለክ"** |
| **አኢመቅ** | **"ለከንቱነት"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ለሐሰት መሐላ"** |

ቃሉ (ቢዲቢ 996) በመሠረቱ ፍችው "ባዶ፣" "ከንቱ፣" ወይም "ምናምንቴነት" ነው። እሱም በብዙ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል (ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት)።

## ልዩ ርዕስ፡ ባዶ፣ ከንቱ፣ ሐሰት፣ ምናምንነት (ቢዲቢ 996)

ይህ ቃል በመሠረቱ ፍችው "ባዶ፣" "ከንቱ፣" "ምናምንነት" ነው

1. መሐላ/የያህዌን ስም በከንቱ ማንሣት – ዘጸ.. 20:7፤ ዘዳ. 5:11፤ 6:13፤ 10:20፤ መዝ. 24:4፤ 139:20
2. ለጣዖታት – መዝ. 31:6፤ ኤር. 18:15፤ ዮናስ 2:8
3. ለንግግር – መዝ. 12:2፤ 41:6፤ 144:8,11፤ ምሳ. 30:8፤ ኢሳ. 59:3፤ ሕዝ. 13:8፤ ሆሴ. 10:4
4. ለሐሳብ – ኢዮብ 15:31፤ ኢሳ. 5:18፤ 30:28
5. ለትንቢት – ኢዮብ 35:13,16፤ ሰቆ. 2:14፤ ሕዝ. 12:24፤ 13:6,7,9,23፤ 22:28
6. ለማይረቡ ሰዎች – ኢዮብ 11:11፤ መዝ. 26:4
7. ለሰዎች ተግባር – መዝ. 60:13፤ 89:48፤ 108:13፤ 127:2
8. የማይረባ መሥዋዕት – ኢሳ. 1:13

ይህ እንደ "ከንቱነት" ተመሳሳይ ቃል አይደለም (BDB 210 I), መክብብ ላይ በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ የዋለ። እሱም መዝሙር ላይ ይከሰታል 31:6፤ 39:5-6,11፤ 62:9፤ 78:33፤ 94:11, 144:4።

▣ ቁ. 4 የእውነተኛ ታማኝ ተከታይ አራት ባሕርያት ካሉት፣ እንዲሁም ሁለተኛው ስንኝ ከሦስተኛው ጋር ትይዩ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ሁለቱም የሚጠቅሱት በፍርድ ቤት የሚቀርብ እውነተኛ ምስክርነትን ነው፣ ቁ.4ለ የጣዖት አምልኮን ከሚጠቅሰው ምትክ። "የጽድቅ" አጠቃቀም፣ በፍርድ ቤት መልኩ (ዝኪ. ቁ. 5ለ) ለዚህ ዋጋ ይሰጣል። ኒዶቲ ቅጽ 3 ገጽ 153 ተመልከት፣ እዚያም "ንጹሕ እጆች" ምናባዊ መሆናቸውን፣ ለፍርድ የንጽሕና ውሳኔ።

**24፡6 “*መፈለግ... መፈለግ*”** እነዚህ በሁለት የተለያዩ ግን ትይዩ በሆኑ የዕብራይስጥ ሥሮች ነው የሚተረጎሙት፡፡

1. ቢዲቢ 205፣ ኬቢ 233፣ አንቀጽ (ኤምቲ — ነጠላ፣ *ቁሪ* — ብዙ)፣ መዝ. 78፡34
2. ቢዲቢ 134፣ ኬቢ 152፣ *ፒይል* አንቀጽ፣ ዘዳ. 4:29፤ 1 ዜና. 16:11፤ 2 ዜና. 7:14፤ መዝ. 27:8፤ 105:4፤ ሆሴ. 3:5፤ 5:15፤ ሶፎ. 1:6፤ 2:3

▣ **“—*የያዕቆብን*”** ይህን ከአንድ መንገድ በላይ መረዳት ይቻላል፡፡

1. የያዕቆብ አምላክ (LXX)
2. እግዚአብሔርን ፈልግ፣ ያዕቆብ እንደፈለገው
3. ሌለኛው ስም ለኪዳኑ ሕዝቦች (እንደ “ትውልድ”)፤ ያዕቆብ = እስራኤል

▣ **“ሴላህ”** መዝ. 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ እና መግቢያ ለመዝሙር VII ተመልከት፡፡

**መዝሙር ፡ 24፡7-10**

**[7]እናንተ መኳንንቶች፥ በሮችን ከፈቱ፥**
**የዘላለም ደጆችም ይከፈቱ፥**
**የክብርም ንጉሥ ይግባ።**
**[8]ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው?**
**እግዚአብሔር ነው፥ ብርቱና ኃያል፥**
**እግዚአብሔር ነው፥ በሰልፍ ኃያል።**
**[9]እናንተ መኳንንቶች፥ በሮችን ከፈቱ፥**
**የዘላለም ደጆችም ይከፈቱ፥**
**የክብርም ንጉሥ ይግባ።**
**[10]ይህ የክብር ንጉሥ ማን ነው?**
**የጭፍሮች አምላክ እግዚአብሔር፥**
**እርሱ የክብር ንጉሥ ነው።** **ሴላህ**

**24፡7-10** ደጆች/የዘላለም ደጆች የሚጠቅሰው የኢየሩሳሌምን ደጆች ነው፣ የመቅደሱን (ቁ. 3)፡፡ እነርሱ ሰውኛ ዘይቤ ሆነዋል፣ ታላቁን የክብር ንጉሥ፣ ያህዌን ለመቀበል፣ ወደ ቤቱ/መቅደሱ ሲመጣ ከድል በኋላ (ዘጸ. 14:14፤ 15:3፤ ዘዳ. 1:30፤ 3:22፣ ማለትም፣ ቅዱስ ጦርነት)፡፡ ማለት የሚቻለው ከኪዳኑ ታቦት ጋር የተያያዘው ድርጊት ተምሳሌትነቱ የያህዌን ዳግም ወደ መቅደሱ መምጣት ነው፡፡ ትእዛዞቹን ሁሉ ተገንዘብ፡፡

1. እናንት መኳንንት አንሡ — ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724፣ ተተኳሪ
2. አንሡ — ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724፣ ተተኳሪ
3. የክብር ንጉሥ ይግባ — ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
4. እናንት መኳንንት አንሡ — ከቁ. 1 ተመሳሳይ
5. አንሡ — ከቁ. 2 ተመሳሳይ፣ ግን ተተኳሪ
6. ከቁ. 3 ተመሳሳይ

የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 241) እንደሚለው ቁጥር 7 አምልኳዊ ልቅሶ ነው፣ ለአምልኮ የሚመጡ መናኞች (ምዕመናን)፡፡ እንደዛ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ቁ. 8 እና 10 የሌዋውያን አምልኳዊ ምላሽ ነው፡፡ እኔ እንደሚመስለኝ ቁጥር 1-6 የሌዋውያንን የአምልኮ ደንብ የሚያሳይ ነው፣ በመቅደሱ ጠባቂዎች የሚባል፡፡

**24፡10** እዚህ ቁጥር ላይ ግሣዊነት የለም፡፡ “የይሆናል” ግሥ የተደረገው ለእንግሊዝኛ ተናጋሪዎች ነው፣ በጥንታዊ ዕብራይስጥ አንባቢዎች እንደተደረገው ሁሉ፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙር 15 እና መዝሙር 24 እንዴት ይዛመዳሉ?
2. “ሐሰተኝነትን” ከብኪ አኳያ ግለጽ።
3. “ፊትህን መፈለግ” ምን ማለት ነው?
4. ቁጥር 7-10 በምን ሁነት የአምልኮ ሥርዓት ላይ ተደጋግሞ የሚባለው?

## መዝሙር 25
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የጥበቃ፣ ምሪት እና ይቅርታ ጸሎት <br> ኤምቲ መግቢያ የዳዊት መዝሙር። | የመታደግና ይቅርታ ልመና | ከግል ጠላቶች መታደግ (ሰቆቃ) | የምሪት እና ጥበቃ ጸሎት | የአደጋ ጊዜ ጸሎት (መስቀልያ) |
| 25:1-3 | 25:1-3 | 25:1-2 | 25:1-3 | 25:1-2ሀ (ኣሌፍ) |
| | | | | 25:2ለ (ቤት) |
| | | | | 25:3 (ጋሜል) |
| | | 25:3 | | |
| 25:4-7 | 25:4-5 | 25:4-5 | 25:4-5 | 25:4 (ዳሌጥ) |
| | | | | 25:5 (ሂ) |
| | 25:6-7 | 25:6-7 | 25:6-7 | 25:6ሐ-7 (ዋው) |
| | | | | 25:6 (ዜይን) |
| | | | | 25:7 (ሄት) |
| 25:8-11 | 25:8-11 | 25:8-10 | 25:8-10 | 25:8 (ቴፍ) |
| | | | | 25:9 (ዮድ) |
| | | | | 25:10 (ካፍ) |
| | | 25:11-15 | 25:11-14 | 25:11 (ላሜድ) |
| 25:12-15 | 25:12-15 | | | 25:12 (ሜም) |
| | | | | 25:13 (ነን) |
| | | | | 25:14 (ሳሜክ) |
| | | | 25:15-18 | 25:15 (ኤን) |
| 25:16-22 | 25:16-21 | 25:16-18 | | 25:16 (ፒ) |
| | | | | 25:17 (ዛዲ) |
| | | | | 25:18 (ቆፍ) |
| | | 25:19-21 | 25:19-21 | 25:19 (ረሽ) |
| | | | | 25:20 (ሺን) |
| | | | | 25:21 (ታው) |
| | 25:22 | 25:22 | 25:22 | 25:22 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### *ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት*

*ሀ. ይህ መስቀልያ ነው (ዝኪ. አኢመቅ አንጓዎች)። ሆኖም፣ ሁለት ፊደላት ጠፍተዋል፣ እንዲሁም ሁለት ተደርበዋል (የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 1309)።*

ለ. እሱም በአጽንዖታዊ የጸሎት ጥያቄዎች የተሞላ ነው።
1. *ተጓዳኞች*
   ሀ. ቁ.2 — "አልፈር፣" ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ *ተደጋጋፊ* (ይህ ሥር በዚህ መዝሙር ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፤ እሱም እጅግ የበዛ አይደለም፣ የታማኝነት ማሳያ እስከሆነ ድረስ)
   ለ. ቁ. 20 — "አልፈር፣" ከሀ ጋር ተመሳሳይ፣ ግን ያልተጠናቀቀ፣ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ (ኢንክሉሲኡ አካታች)
2. ያልተጠናቀቁ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ
   ሀ. ቁ. 2 — "ጠላቶቼም በእኔ ላይ ደስ አይሰኙ፣" ቢዲቢ 763፣ ኬቢ 836፣ ያልተጠናቀቀ
   ለ. ቁ. 7 — "ኃጢአትን አታስብ፣" ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ ያልተጠናቀቀ (ይህ ሥር ቁ. 6-7 ላይ ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል)
   ሐ. ቁ. 21 — "የውሃትና ቅንነት ይጠብቁኝ፣" ቢዲቢ 665፣ ኬቢ 718፣ ያልተጠናቀቀ
3. ተተኳሪዎች
   ሀ. ቁ. 4 – "መንገድህን አሳውቀኝ፣" ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ ሂፊል
   ለ. ቁ. 4 – "ፍለጋህን አስተምረኝ፣" ቢዲቢ 540፣ ኬቢ 531፣ ፔል
   ሐ. ቁ. 5 – "በእውነትህ ምራኝ፣" ቢዲቢ 201፣ ኬቢ 231፣ሂፊል
   መ. ቁ. 5 – "አስተምረኝ፣" ከለ ጋር ተመሳሳይ
   ሠ. ቁ. 6 – "አስብ፣" ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 268፣ቃል
   ረ. ቁ. 7 – "አስብ፣" ከሠ ጋር ተመሳሳይ
   ሰ. ቁ. 16 – "ፊትህን ወደ እኔ አድርግ፣" ቢዲቢ 815፣ ኬቢ 937፣ ቃል
   ሸ. ቁ. 16 – "ማረኝም፣" ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334፣ ቃል
   ቀ. ቁ. 17 – "ከጭንቀቴ አውጣኝ፣" ቢዲቢ 422፣ ኬቢ 425፣ ሂፊል
   በ. ቁ. 18 – "መከራዬን እይ፣" ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ ቃል
   ተ. ቁ. 18 – "ኃጢአቴን ሁሉ ይቅር በል፣" ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 1157፣ ቃል
   ቸ. ቁ. 19 – "ጠላቶቼን እይ፣" ከበ ጋር ተመሳሳይ።
   ኀ. ቁ. 20 – "ነፍሴን ጠብቃት፣" ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ ቃል
   ነ. ቁ. 20 – "አድነኝ፣" ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ ሂፊል
   ኘ. ቁ. 22 – "እስራኤልን አድነው፣" ቢዲቢ 804፣ ኬቢ 911፣ ቃል

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 25፥1-3**
**[1]አቤቱ፥ ወደ አንተ ነፍሴን አነሣለሁ።**
**[2]አምላኬ፥ አንተን ታመንሁ**
**አልፈር፥**
**ጠላቶቼ በእኔ አይሣቁብኝ።**
**[3]አንተን ተስፋ የሚያደርጉ አያፍሩም**
**በከንቱ የሚገበዙ ያፍራሉ።**

**25፥1-3** *መዝሙረኛው በጠላቶቹ እንዳያፍር ሰግቷል ነገር ግን በፍራቻው መሐል በያህዌ ላይ ያለውን የተስፋ ድል እምነቱን ይገልጻል።*

እሱም ባሕርዩን ያደረገው
1. ነፍሱን ወደ ያህዌ ማንሣት — ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ እሱም ቀጣይነት ያለውን ድርጊት የሚገልጽ (መዝ. 86:4፤ 143:8)
2. በያህዌ መታመን – ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ እሱም የጸና ድርጊትን/ሁኔታን የሚያሳይ
3. ያህዌን ይጠብቃል – ቢዲቢ 875፣ ኬቢ 1082፣ *ቃል* አንቀጽ፣ ኤቢ (ገጽ. 155) የሚለው እሱ ከሌላ ሥር መሆኑን ነው፣ ከተመሳሳይ ፊደላት፣ ፍቻቸውም "መጥራት" ወይም "መጠየቅ"

ከዚህ የተነሣ እሱ ታምኗል፣
ሀ. እንደማያፍር (አካታች፣ መዝ. 25፡20፤ 31፡1)
ለ. በ...ላይ እንደሚደሰት (መዝ. 41፡11)

ነገር ግን ጠላቶቹ ይሆንባቸዋል (ዝኪ. ቁ. 3ለ)። በዚህ መልኩ በያህዌ የሚታመኑ የእሱ ባሕርይ ምስክሮች ናቸው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት፣ መዝ. 9፡10ለ ላይ)። እነርሱ እንዴት እንደሚኖሩና እንደሚታመኑ ለያህዌ እውነታና ባሕርይ ጽኑ የሆነ ማስረጃ ይሰጣል።

**25:3**

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **የተእመቅ** | **"በከንቱ"** |
| **አየተመት፣ LXX** | **"ያለ ምክንያት"** |
| **አኢመቅ** | **"ያለ መነሻ"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"እንዲያው፣ ያለምክንያት"** |
| **አእት መጽሐፍ ቅዱስ** | **"ያለ ውጤት"** |
| **ፔሺታ** | **"ከንቱ"** |

ይህን ቅጽል (ቢዲቢ 938፣ ኬቢ 1229) በሁለት መንገድ መረዳት ይቻላል።

1. ያለምክንያት (መዝ. 7:4)
2. ያለ ውጤት (ኢሳ. 55:11፤ ኤር. 50:9)

**መዝሙር ፡ 25፡4-7**

**4አቤቱ፥ መንገድህን አመልክተኝ፥**
**ፍለጋህንም አስተምረኝ።**
**5አንተ የመድኃኒቴ አምላክ ነህና**
**በእውነትህ ምራኝ፥ አስተምረኝም**
**ቀኑን ሁሉ አንተን ተስፋ አድርጌአለሁ።**
**6አቤቱ፥ ምሕረትህንና ቸርነትህን አስብ፥**
**ከጥንት ጀምሮ ናቸውና።**
**7የልጅነቴን ኃጢአትና መተላለፍ አታስብብኝ**
**አቤቱ፥ ስለ ቸርነትህ ብዛት**
**እንደ ምሕረትህ አስበኝ።**

**25፡4-7** ብርቱዎቹ ተለጣጣቂ አጽንዖታዊ ተተኳሪዎችን ተገንዘብ፣ እነርሱም የያህዌን ድርጊት የሚጠይቁ፣ በእርሱ በሚታመነው አኳያ።

1. *ማወቅ* (ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ *ሂፊል ተተኳሪ*) *መንገዶቹን* (ቢዲቢ 202፣ *መዝ.* 25:4፣8፣9፣12)
2. *ማስተማር* (ቢዲቢ 540፣ ኬቢ 531፣ *ፔይል ተተኳሪ*) *መንገዶቹን* (ቢዲቢ 73፣ ዝኪ. 25:4፣10)
3. *መምራት* (ቢዲቢ 201፣ ኬቢ 231፣ *ሂፊል ተተኳሪ*) እሱን በእውነቱ (ቢዲቢ 54፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ *መዝሙር* 12:1 ላይ)
4. *ማስተማር* (ቢዲቢ 540፣ ኬቢ 531፣ *ፔይል ተተኳሪ*) እኔን

አንዱ የሚታመን (እና የሚጠብቅ፣ ቁ. 5ሐ፣ 21ለ) ያህዌን ለማወቅ ይሻል፣ በሁለቱም በግል ኅብረት እና በተገለጠ እውነት። በዚህ እውነት ላይ በመመሥረት እና በሕይወት ስልት መታዘዝ ይጠይቃል፣ ማለትም ያህዌ

1. ባሕርዩን ያስባል (ዝኪ. ቁ. 7ለ፣ሐ)፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት *መዝ.* 9:10ለ
   ሀ. ርኅራኄ – ቢዲቢ 933 (ቁ. 5)
   ለ. ቸርነት – ቢዲቢ 338 (ዝኪ. ቁ. 6፣7፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት *መዝ.* 5:7)
   ሐ. መልካምነት – ቢዲቢ 375 (ቁ. 7)
2. ኃጢአትን አታስብ (ቢዲቢ 308) የልጅነቱን (ኢዮብ 13:26)
3. መተላለፉን እንዳያስብ (ቢዲቢ 833)

**25፡4 "መንገድ... ፍለጋዎች"** የተገለጠው የያህዌ እውነት በመልካም ሁኔታ ይታያል፣ በምልክት/በሚታይ መንገድ ወይም ፍርድ መዝ. 1፡1 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት)። ምን ማድረግ እንደሚኖር ውዥንብር የለም፣ በሚገባ ሁኔታ ለተገለጠው መንገድ መታዘዝ ብቻ ነው የሚያስፈልገው (መዝ. 139፡24)። የእግዚአብሔር መንገድ ዘወትር የሚገለጸው እንደ ተስተካከለ፣ ቀጥተኛ፣ ግልጽ፣ በግልጽ የሚታይ ነው።

**25፡6 "ከጥንት ጀምሮ ናቸውና"** *መዝሙረኛው ያህዌን ይጠይቃል*፣ በእርሱ በኩል እንዲሠራ (እና እስራኤል፣ ዝኪ. ቁ. 22) ቋሚ በሆኑ መንገዶች፣ ባለፉት ጊዜያት ባደረገው (መዝ. 89፡49)። በዋነኛነትም መዝሙረኛው፣ የኪዳኑ አምላክ የኪዳኑን ተስፋዎች እንዲያስታውስ ይሻል። እሱ በቀድሞ ጊዜ አድርጓል፣ አሁንም እባክህን እንደገና ለሕዝብህና ለዓላማህ አድርግ። ምንም እንኳ መዝሙረኛውና እስራኤል በስንፍና ኃጢአት ቢሠሩም፣ እባክህን የኪዳን ፍቅርህ (*ሄሰድ፣ ማለትም፣ የኪዳን ታማኝነት*) እና ያንተ መሠረታዊ ባሕርይ (ማለትም፣ ቸርነትና ምሕረት፣ መዝ. 23፡6)፣ የተዋረደውን ኃጢአተኛ ይቅር በል (ዝኪ. ቁ. 8-11)።

***መዝሙር ፡ 25፡8-11***

**[8]እግዚአብሔር ቸር ቅንም ነው**
**ስለዚህ ኃጢአተኞችን በመንገድ ይመራቸዋል።**
**[9]ገሮችን በፍርድ ይመራል፥**
**ለገሮችም መንገድን ያስተምራቸዋል።**
**[10]የእግዚአብሔር መንገድ ሁሉ ቸርነትና እውነት ነው።**
**ቃል ኪዳኑንና ምስክሩን ለሚጠብቁ።**
**[11]አቤቱ፥ ኃጢአቴ እጅግ ነውና**
**ስለ ስምህ ይቅር በለኝ።**

**25፡8-11** አብዛኞቹ ቁልፍ ቃላትና ጽንሰ-ሐሳቦች ከቁ. 4-7 እዚህ አንዷ ላይ ተደግመዋል። ይህ መስቀልያ መዝሙር እንደሆነ አስታውሱ። ሁሉም የመዝሙረኛው ቅኔአዊ ፍቃድ እና የፈጠራ ብልሃት ጥቅም ላይ ውሏል።

1. 25፡8ሀ የያህዌን ባሕርይ ያከብራል፣ ቁ. 6፣7 ላይ እንዳደረገው
   ሀ. መልካም (ቢ.ዲ.ቢ. 373)
   ለ. ቅን (ቢ.ዲ.ቢ. 449)
2. 25፡8ለ-9 እንደገና የያህዌን ትምህርትና ምሪት ይጠቅሳል፣ ቁ. 4-5 ላይ እንዳደረገው

ሁለቱ ተጨማሪ አስተሳሰቦች ገላጭ ቃላት ናቸው፣ ስለ አንዱ ሐሳብና ምሪት።

1. ኃጢአተኞች (ቢ.ዲ.ቢ. 308)፣ ቁ. 8
2. ትሑት (ቢ.ዲ.ቢ. 776)፤ ቁ. 9 (ሁለቴ)

የያህዌ መንገዶች በባሕርያቸው

1. ቸርነት (ዝከ. ቁ. 6፣7)
2. እውነት (ዝከ. ቁ. 5)

**25፡10 *"መንገድ... ምስክር"*** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር ራዕይ ቃላት፣ መዝሙር 1፡2 ላይ።

▣ ***"ቃል ኪዳኑን ለሚጠብቁ"*** አጽንዖቱን ተገንዘቡ፣ በእውቀት ሳይሆን (ዝከ. 25፡4-5) ግን በመታዘዝ (ዘዳ. 5፡10፤ 6፡5፤ 7፡9፤ 10፡12፤ 11፡1፣13፣22፤ 13፡3፤ 19፡9፤ 30፡6፣16፣20፤ መዝ. 103፡18)። መታዘዝ የተቀባይነትና የይቅርታ ብልሃት አይደለም፣ እሱም ያየህዌ፣ ነገር ግን እሱን የመገናኘትና የእሱን ፍቃድ መረዳት እንጂ። ኢየሱስ እንደዚያ ብሏል፣ ሉቃስ 6፡46 ላይ፣ ደግሞም ኤፌ. 2፡8-9 እና ከዚያም 1፡ 4፤ 2፡10 ተመልከት። ጸጋ ዘወትር ቀዳሚ ነው (ዝከ. 25፡11)! እሱን መቀበል የሚቻለው በእምነት ነው፣ ነገር ግን እምነቱ የሚኖርበት መሆን አለበት (ያዕቆብ 2፡14-26)።

▣ ***"ኪዳን"*** ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ ኪዳን (ברית)

የብሉይ ኪዳን ቃል የሆነው ቤሪዝ (ቢ.ዲ.ቢ. 136) ኪዳን፣ ለመግለጽ ቀላል አይደለም። በዕብራይስጥ የሚገጥም ግሥ የለውም። ሥርወ ቃላዊ ፍች ለማምጣት የተደረጉት ሙከራዎች ሁሉ የማያሳምኑ ሆነዋል። ሆኖም፣ የጽንሰ ሐሳቡ ማዕከላዊነት የቃሉን አጠቃቀም ይመረምሩ ዘንድ ሊቃውንትን አስገድዷቸዋል፣ ተግባራዊ ፍችውን ለመወሰን።

ኪዳን አንዱ እውነተኛው አምላክ የእሱ ፍጡር ከሆነው ሰው ጋር የሚደረግ ውል ነው። የኪዳን ጽንሰ ሐሳብ፣ ውል፣ ወይም ስምምነት የመጽሐፍ ቅዱስን መገለጥ ለመረዳት ወሳኝነት አለው። በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰው ልጆች ነጻ ፍቃድ መካከል ያለው ክርክር በኪዳን ጽንሰ ሐሳብ በግልጽ ይታያል። አንዳንድ ኪዳናት የተመሠረቱት ግላዊ በሆኑ በእግዚአብሔር ባሕርይ እና ድርጊት ላይ ነው።

1. ተፈጥሮ ራሱ (ዘፍ. 1-2)
2. የአብርሃም መጠራት (ዘፍ. 12)
3. ከአብርሃም ጋር ኪዳን (ዘፍ. 15)
4. የኖህ መጠበቅና ተስፋ (ዘፍ. 6-9)

ሆኖም፣ የኪዳን ዋነኛ ባሕርዩ ምላሽን መፈለጉ ነው

1. በእምነት አዳም እግዚአብሔርን መታዘዝ ነበረበት፣ በኤደን ገነት መሐል ከሚገኘው ዛፍ መብላት የለበትም
2. በእምነት አብርሃም ወገኖቹን ትቶ፣ እግዚአብሔርን መከተል፣ እንዲሁም ስለ መጪው ዝርዮቹ ማመን ነበረበት
3. በእምነት ኖህ ትልቅ መርከብ ገንብቶ፣ ከውሃ ራቅ ያለ፣ እንስሳትን ማሰባሰብ ነበረበት፡፡
4. በእምነት ሙሴ እስራኤላውያንን ከግብፅ አውጥቶ የተወሰኑ መመሪያዎችን ፣ ለሃይማኖታዊና ለማህበራዊ ሕይወት የሚሆኑ፣ የበረከትና የርግማን ተስፋዎችን መቀበል ነበረበት (ዘዳ. 27-29)። ተመሳሳይ የሆነ ክርክር እግዚአብሔር ከሰዎች ጋር ስላለው ግንኙነት "በአዲስ ኪዳን" ተመልክቷል። ክርክሩ በግልጽ የሚታየው ሕዝ. 18ን ከሕዝ. 36፡27-37 ጋር በማወዳደር ነው የያህዌ ድርጊት። ኪዳኑ የተመሠረተው በእግዚአብሔር የጸጋ ድርጊት ነውን ወይስ ለሰው በተሰጠ የውክልና ሃላፊነት? ይህ አንገብጋቢ ጉዳይ ነው፣ በብሉይ ኪዳን፣ በአዲሱም ጭምር። የሁለቱም ግቦች ተመሳሳይ ናቸው፡ (1) የጠፋው ኅብረት መመለስ፣ ዘፍ. 3 እና (2) የእግዚአብሔርን ባሕርይ የሚያንጸባርቅ ጻድቅ ሕዝብ መመሥረት።

የኤር. 31፡31-34 አዲስ ኪዳን ክርክሩን ያቃልላል፣ የሰዎችን ድርጊት ተቀባይነት ለማግኘት የሚደረገውን በማስቀረት። የእግዚአብሔር ሕግ ውስጣዊ መሻት ሆነ፣ ውጫዊ የሕግ ቁጥር ቀርቶ። መልካም፣ ጻድቅ ሕዝብ የመሆን ግብ በተመሳሳይ መልኩ ነው የሚቀረው፣ ነገር ግን ዘዴው (አገባቡ) ነው የተቀየረው። የወደቀው የሰው ልጅ የእግዚአብሔር አምሳል ነጸብራቅ ከመሆን ብቃት እንደሌለው ተረጋግጧል። ችግሩ ኪዳኑ አልነበረም፣ ነገር ግን የሰው ሃጢአተኝነትና ድካም ነው (ሮሜ 7፤ ገላትያ 3)።

ተመሳሳይ ክርክር በብሉይ ኪዳን ሁኔታዊ ያልሆነና በሁኔታዊ ኪዳናት መካከል እንዳለ ይኖራል፣ በአኪ። ደኅንነት በፍጹም ነጻ ነው በኢየሱስ ክርስቶስ የተፈጸመ ሥራ፣ ነገር ግን ንስሐና እምነትን ይጠይቃል (ሁለቱንም በመነሻነትም ሆነ በቀጣይነት)። እሱም ሁለቱም፣ ሕጋዊ ሥልጣናዊ አዋጅና ክርስቶስን ወደ መምሰል መጠራት፣ አመላካች መግለጫ ለተቀባይነትና አስፈላጊ ቅድስና! አማኞች በራሳቸው ድርጊት የዳኑ አይደሉም፣ ነገር ግን በመታዘዝ (ኤፌ. 2፡8-10)። እግዚአብሔርን በመምሰል መኖር የመዳን ማስረጃ ነው እንጂ የመዳን ምክንያት አይደለም። ሆኖም፣ የዘላለም ሕይወት ሊስተዋሉ የሚችሉ ባሕርያት አሉት! ይህ ክርክር በዕብራውያን መጽሐፍ ላይ በግልጽ ይታያል።

**25፡11** ማንኛውም የይቅርታ ተስፋ የተመሠረተው በማይለወጠው በያህዌ ባሕርይ ላይ ነው (መዝ. 102፡26-27፤ ሚልክያስ 3፡6፤ ያዕቆብ 1፡17፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ.. 9፡10ለ ላይ) እና በመሢሑ (ዕብ. 13፡8)። ይኸውም ከእርሱ ስም እና ባሕርይ የተነሣ ነው (መዝ. 79፡9)።

◘ **"እጅግ ነውና"** አንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ከተረዳን (ማለትም፣ ቅድስና፣ ሌዋ. 19፡2፤ ማቴ. 5፡48) እና የእግዚአብሔርን እውነት፣ ኃጢአታችንና የእርሱም ውጤት በተሻለ ማስረጃ ይሆነናል። መልካሙንና ክፉውን የሚያስታውቀውን ዛፍ (ዘፍጥረት 3) የዓመጸኝነታችንንና የውጤቱን መገለጥ አመጣ!

**መዝሙር ፡ 25፡12-15**

**12እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ማን ነው?**
**በሚመርጠው መንገድ ያስተምረዋል።**
**13ነፍሱ በመልካም ታድራለች፥**
**ዘሩም ምድርን ይወርሳል።**
**14እግዚአብሔር ለሚፈሩት ኃይላቸው ነው፥**
**ቃል ኪዳኑንም ያስታውቃቸዋል።**
**15እርሱ እግሮቼን ከወጥመድ ያወጣቸዋልና**
**ዓይኖቼ ሁልጊዜ ወደ እግዚአብሔር ናቸው።**

**25፡12-15** እንደ 4-7 እና 8-11 አንጓዎች፣ ተመሳሳይ የሆኑ ጭብጦች እዚህም ቀጥለዋል። ታማኝ ተከታይ ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳለው ተገንዘብ።

1. ያህዌን ይፈራል፣ ቁ. 12፣14፣ መዝ. 15፡4፤ 103፡11፣13፤ 115፡11፤ 118፡4
2. የያህዌን ኪዳን ያውቃል፣ ቁ. 14
3. ዓይኖቹ ዘወትር በያህዌ ላይ ናቸው፣ ቁ. 15

ያህዌ ለእርሱ እንደሚያደርግለት ተገንዘብ።

1. በመንገድ ያስተምረዋል፣ ቁ. 12፣ መዝ. 16፡11፤ 139፡24
2. መልካምን ይሰጣል (ቢ.ዲ.ቢ. 373) ለእርሱና ለዘሩ፣ ቁ. 13
3. እውነቱን ይገልጥለታል፣ ቁ. 14
4. እሱ እግሮቹን በመንገዱ ይመራዋል፣ ከጉዳትም ይጠብቀዋል፣ ቁ. 15

**25፡12 "በመረጠው"** በመጽሐፍ ቅዱስ ሥነ-መለኮታዊ ሚዛን አለ፣ በያህዌ ሉዓላዊ ድርጊቶች እና ሰዎች እሱንና የእሱን መንገዶች እንዲመርጡ በሚጠይቀው መካከል (ዘዳ. 30፡15፣19፤ ኢያ. 24፡14-15)። በምርጫዎቻችን ኃላፊነት አለብን! ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ መመረጥ/ቅድመ ውሳኔ (መታደል) እና የሥነ መለኮት ሚዛን አስፈላጊነት

መመረጥ አስደናቂ መሠረተ እምነት ነው። ሆኖም፣ እሱ የውዴታ ጥሪ አይደለም፣ መተላለፊያ መስመር የመሆን ጥሪ እንጂ፣ ለሌሎች መዋጀት መሣርያ ወይም ምክንያት! በብሉይ ኪዳን ቃሉ በቀዳሚነት ጥቅም ላይ ይውል የነበረው ለአገልግሎት ነበር፤

በአዲስ ኪዳን ጥቅም ላይ የዋለው ለደህንነት ነው፣ እሱም ከአገልግሎት በተያያዘ። መጽሐፍ ቅዱስ ተቃርኖ ያለው የሚመስለውን የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነትና የሰውን ነጻ ፍቃድ አያስታርቅም፣ ሁለቱንም ያጸናል እንጂ! ለመጽሐፍ ቅዱስ የተሻለ ክርክር ሊሆን የሚችለው ሮሜ 9ነው፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊ ምርጫ እና ሮሜ 10 በሰው ልጅ ምላሽ አስፈላጊነት (ዝከ 10፡11፣13)።

ለዚህ ሥነመለኮታዊ ክርክር ቁልፉ ሊገኝ የሚችለው በኤፌሶን 1፡4 ነው። ኢየሱስ በእግዚአብሔር የተመረጠ ሰው ነው እንዲሁም ሁሉም በእሱ ሃይል የተመረጡ ናቸው (ካርል ባርዝ)። ኢየሱስ የእግዚአብሔር "አዎን" ነው ለወደቀው የሰው ልጅ ፍላጎት (ካርል ባርዝ)። ኤፌሶን 1፡4 ደግሞ ጉዳዩን ለማብራራት እገዛ የሚያደርገው የቅድመ መታደል ግብ ሰማይ አለመሆኑን ነው፣

ቅድስና እንጂ (ክርስቶስን መምሰል)። ዘወትር በወንጌል ጠቀሜታ እየተሳብን፣ ሃላፊነታችንን ችላ እንላለን! የእግዚአብሔር ጥሪ (ምርጫ) ለጊዜው እንዲሁም ለዘላለም ነው!

መሠረተ እምነቶች ከሌሎች እውነቶች ጋር ለመያያዝ ነው የሚመጡት እንጂ፣ ለተናጠላዊ፣ ለማይያያዙ እውነቶች አይደለም። የተሻለ ምስያ የሚሆነው ህብረ ከዋክበትና አንድ ነጠላ ኮከብ ነው። እግዚአብሔር እውነትን ያቀረበው በምስራቅ ዘውግ እንጂ በምዕራብ አይደለም። እኛ ክርክሮቹን ልናስወግዳቸው አይገባም፣ በተቃርኗዊ (አያዎ (ፓራዶክስ)) ጥንዶች የቀረቡትን መሠረተ እምነታዊ እውነቶች፡

1. ቅድመ መታደል ወይም የሰዎች ነጻ ፍቃድ
2. የአማኞች ድኅነት ወይም ወይም የጥረት አስፈላጊነት
3. የመነሻ ኃጢአት ወይም የፍቃድ ኃጢአት
4. ኃጢአት የለሽነት (ፍጽምና) ወይም ባነስተኛ ኃጢአት መሥራት
5. ከመነሻው የሚሆን ጽድቅ እና ቅድስና ወይም ቀጣይነት ያለው ቅድስና
6. ክርስቲያናዊ ነጻነት ወይም ክርስቲያናዊ ኃላፊነት
7. የእግዚአብሔር ከአዕምሮ በላይ መሆን ወይም የእግዚአብሔር በወሰን ውስጥ መሆን
8. እግዚአብሔር መዳረሻው የማይታወቅ መሆኑ ወይም እግዚአብሔር በቅዱስ ቃሉ ሊታወቅ መቻሉ
9. የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን እንዳለ ወይም ወደፊት እንደሚቀዳጁት
10. ንስሐ እንደ እግዚአብሔር ስጦታ ወይም ንስሐ በሰው ልጆች ምላሽ በኩል አስፈላጊ የሆነ
11. ኢየሱስ እንደ መለኮት ወይም ወይም ኢየሱስ እንደ ሰው
12. ኢየሱስ ከአብ ጋር እኩል ስለመሆኑ ወይም ኢየሱስ የአብ ረዳት ስለ መሆኑ

"የኪዳን" ሥነ መለኮታዊ ጽንሰ ሐሳብ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊነት (ዘወትር መነሻውን የሚወስደውና አጀንዳውን የሚያዘጋጀው) ከ አስገዳጅ መነሻ እና ቀጣይነት ካለው ንስሐ፣ ከሰዎች ከሚፈለግ የእምነት ምላሽ። ጽሑፍን ከማጥራት ተጠበቁ፣ አንደኛውን የፓራዶክስ ጎን ብቻ ከመመልከት እና ሌለኛውን ከማንኳሰስ! የራሳችሁን ተወዳጅ መሠረተ እምነት ብቻ ወይም የሥነ መለኮት ሥርዓት ከማስረዳት ተጠንቀቁ!

**25:14**
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **አኢመቅ** | **"ምሥጢር"** |
| **አየተመት** | **"ወዳጅነት"** |
| **አእቅ** | **"ወዳጅ"** |
| **LXX** | **"ኃይል"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ምክር"** |
| **የተእመቅ** | **"ምክር"** |

የዕብራይስጡ ቃል (ቢዲቢ 691፣ ኬቢ 745) ሊል የሚችለው (ኢዮብ 15:8፤ መዝ. 111:1)

1. የግል ውይይት – ኢዮብ 29:4፤ መዝ. 55:14
2. ምሥጢራዊ ምክር – ኢዮበ 15:8፤ ምሳ. 11:13፤ 20:19፤ 25:9
3. ምሥጢራዊ ክበብ – መዝ. 89:7፤ ኤር. 15:17፤ 23:18፣22

እነዚህ ትርጉሞች ተቀያያሪና ተለዋዋጭ ናቸው። ልዩ የሆነ ምክክር፣ ኅብረት፣ እና የእውቀት ሽግግር በኪዳናዊው አምላክ እና በታማኝ ተከታዮቹ መካከል አለ።

**25፡15** የያህዌ ዓይኖች (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 2፡4-6 ላይ) በሚፈሩት እና በሚታዘዙት ላይ ዘወትር እንደሆኑ፣ እንዲሁ ደግሞ፣ ታማኝም በታማኝነቱ ይቀጥላል፣ ሙሉ እና ተተኳሪ ሐሳቡን በእርሱ ላይ በማድረግ (ዕብ. 12፡2)!

**መዝሙር ፡ 25፡16-22**

**16 እኔ ብቻዬንና ችግረኛ ነኝና**
**ፊትህን ወደ እኔ አድርግ ማረኝም።**
**17 የልቤ ችግር ብዙ ነው**
**ከጭንቀቴ አውጣኝ።**
**18 ድካሜንና መከራዬን እይ፥**
**ኃጢአቴንም ሁሉ ይቅር በለኝ።**
**19 ጠላቶቼ እንደ በዙ እይ፥**
**የግፍም ጥል ጠልተውኛል።**
**20 ነፍሴን ጠብቅና አድነኝ**
**አንተን ታምኛለሁና አልፈር።**
**21 አንተን ተስፋ አድርጌአለሁና**
**የውሃትና ቅንነት ይጠብቁኝ።**

**[22]አቤቱ፥ እስራኤልን**
**ከመከራው ሁሉ አድነው።**

**25፡16-21** ይህ አንጓ የመዝሙረኛውን ችግሮች ይዘረዝራል።

1. ብቻዬን ነኝ
2. ተቸግሬአለሁ
3. ልቡ ችግር አለበት
4. በጭንቀት ውስጥ ነው
5. ጠላቶቹ ብዙዎች ናቸው
6. በጽኑ ቁጣ ጠልተውታል
7. ኀፍረትን ፈርቷል

በእነዚህ ነገሮች አኳያ ያህዌን ይጠይቃል

1. ወደ እርሱ ዞር እንዲል (ማለትም፣ አትኩሮት እንዲሰጠው፣ መዝ. 69፡16፤ 86፡16)
2. ቸር እንዲሆንለት
3. እንዲመለከተው/የእርሱን ችግር እንዲረዳ
4. ኃጢአቱን ይቅር እንዲል (ዝኪ. 25:18፤ መዝ. 32:1፤ 51:2፤ 103:3)
5. ነፍሱን እንዲጠብቅ (መዝ. 86፡2)
6. እንዲያድነው

ያህዌ እነዚህን ነገሮች የሚያደርግለት ምክንያቶቹ

1. በያህዌ በመታመኑ
2. እሱ ያስረግጣል፣ የራሱ ወይም የያህዌ ቅንነትና ጽድቅ (በ25፡18ለ ምክንያት ይህን እንደ ያህዌ ባሕርያት አድርጎ መውሰድ ይሻላል። ኤቢ (ገጽ 159) ይላል፣ እነርሱ በሰውኛ ዘይቤ የቀረቡ የያህዌ ባሕርያት ናቸው)
3. እሱ ያህዌን ይጠብቃል (መዝ. 25፡3)

**25፡22** ይህ የተለየ የመዝጊያ ቃል ይመስለኛል (ከአንድ ቁጥር ወዲያ፣ መስቀልያ ፈርጅ)። ንጉሡ ሕዝቡን ይወክላል። ይህ የመዝሙረኛው የመጨረሻ የጸሎት ጥያቄ ነው፣ እናም በደረጃው ብሔራዊ ነው። ዋጅ (ቢዲቢ 804፣ ኬቢ 911፣ ተተኳሪ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 19:14 ላይ) የእናንተ የኪዳን ሕዝብ (ማለትም፣ "እስራኤል")፣ ለዘላለማዊው የመዋጀት ዓላማህ (ልዩ ርዕስ መግቢያ ለመዝሙር 2 ተመልከት)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወስን አይደለም።

1. ቁጥር 4-7 ያሉትን የጸሎት ጥያቄዎች ዘርዝር።
2. የመዝሙረኛውን ችግሮች ዘርዝር፣ ቁጥር 16-21።
3. የዚህን መዝሙር መልእክት እንዴት ታጠቃልላለህ?
4. ይህንን መዝሙር እንዴት በሕይወትህ ትተገብረዋለህ?

## መዝሙር 26
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የቅንነት ተቃውሞ እና የጥበቃ ጸሎት <u>ኤምቲ መግቢያ</u> የዳዊት መዝሙር | የመለኮታዊ ደኅንነትና የመዋጀት ጸሎት | ከግል ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት (ሰቆቃ) | የመልካም ሰው ጸሎት | የፍጹም ሰው ጸሎት |
| 26:1-7 | 26:1-5 | 26:1-3 | 26:1-3 | 26:1 |
| | | | | 26:2 |
| | | | | 26:3 |
| | | 26:4-5 | 26:4-5 | 26:4-5 |
| | 26:6-8 | 26:6-7 | 26:6-7 | 26:6-8 |
| 26:8-12 | | 26:8-10 | 26:8-10 | |
| | 26:9-10 | | | 26:9-10 |
| | 26:11-12 | 26:11-12 | 26:11 | 26:11-12 |
| | | | 26:12 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር፣ እንደ አብዛኞቹ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ፣ የተመሠረተው በብኪ ጽንሰ-ሐሳብ ላይ ነው፣ "ሁለቱ መንገዶች" በሚባለው (ዘዳ. 30፡ 15፣19፤ መዝሙር 1)። የያህዌን ቃል ለሚያከብሩ ብልጥግና አለ፣ እንዲሁም ኩነኔ ለማያከብሩት (ማለትም፣ የሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-29 ርግማንና ባርኮት)።

ለ. መዝሙረኛው ባጠቃላይ በአንዳንድ የኪዳን መተላለፎች ተከስሷል። የተሻለ ግምት የሚሆነው ጣዖት አምልኮ ነው።

ሐ. ቁጥር 9 የሚያመለክተው የፍጻሜ ዘመን መለያየትን ነው፣ በታማኝና በማይታመን መካከል። ከሕይወት በኋላ በብኪ አሻሚ ጽንሰ-ሐሳብ ነው (ኢዮብ 14:7-12፣13-14፤ 19:25-27፤ መዝ. 16:10፤ 49:15፤ 73:24፤ ኢሳ. 25:8፤ 26:19፤ ዳን. 12:1-4) ነገር ግን ቀጣይነት ያለው መገለጥ (ማለትም፣ አኪ) ጉዳዩን ግልጽ ያደርገዋል (ማቴ. 25:46፤ ዮሐንስ 5:29፤ ሐዋ. 24:15፤ 1 ቆሮንቶስ 15)።

**ልዩ ርዕስ፡ ትንሣኤ**

*ሀ. የትንሣኤ ማስረጃዎች*

1. ሃምሳ (50) ቀናት ከጰንጠቆስጤ በኋላ፣ ትንሣኤ የጴጥሮስ ስብከት ቁልፍ ማስታወሻ ሆነ (ሐዋ. 2)። ሺዎች በስፍራው ይኖሩ የነበሩ፣ ሊፈጸም የተመለከቱ አምነዋል!
2. የደቀ-መዛሙርት ሕይወት ተስፋ ከመቁረጥ ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ ተለውጧል (ትንሣኤን አልጠበቁም ነበር) ግልጽ በሆነ፣ ይልቁንም በሰማዕትነት።

ለ. የትንሣኤ ጠቀሜታ
1. ኢየሱስ እሱ መሆኑን ያመለክታል (ማቴ. 12፡38-40 ሞትና ትንሣኤውን እንደተነበየው)
2. እግዚአብሔር ማጽደቁን አስቀምጧል፣ በኢየሱስ ሕይወት፣ ትምህርት፣ እና የምትክነት ሞት! (ሮሜ 4፡25)
3. የሁሉንም ክርስቲያኖች ተስፋ ያሳየናል (ማለትም፣ የትንሣኤ አካላት፣ 1ቆሮንቶስ 15)

ሐ. የኢየሱስ ቃል፣ ከሙታን እንደሚነሣ ያለው
1. ማቴ. 12:38-40፤ 16:21፤ 17:9፣22፣ 23፤ 20:18-19፤ 26:32፤ 27:63
2. ማርቆስ 8:31፤ 9:1-10፣ 31፤ 14:28፣58
3. ሉቃስ 9:22-27
4. ዮሐንስ 2:19-22፤ 12:34፤ ምዕራፍ 14-16

መ. ተጨማሪ ጥናት
1. *Evidence That Demands a Verdict* by Josh McDowell (ፍርድ የሚጠይቀው ማስረጃ)
2. *Who Moved the Stone?* by Frank Morrison (ድንጋዩን ማን አነሣው?)
3. *The Zondervan Pictorial Encyclopedia of the Bible*፣ "Resurrection፣" "Resurrection of Jesus Christ" (ዞንደርቫን ስዕላዊ የመጽሐፍ ቅዱስ ኢንሳይክሎፒዲያ፣ "ትንሣኤ፣" "የኢየሱስ ክርስቶስ ትንሣኤ")
4. *Systematic Theology* by L. Berkhof፣ (ስልታዊ ሥነ-መለኮት) ገጽ 346፣ 720።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 26፡1-7**

**1አቤቱ፥ እኔ በየውሃቴ ሄጃለሁና ፍረድልኝ**
**በእግዚአብሔርም አምኛለሁና አልናወጥም።**
**2አቤቱ፥ ፍተነኝ መርምረኝም**
**ኵላሊቴንና ልቤን ፍተን።**
**3ምሕረትህ በዓይኔ ፊት ነውና፥**
**በእውነትህም ተመላለስሁ።**
**4በከንቱ ሸንጎ አልተቀመጥሁም፥**
**ከዓመፀኞችም ጋር አልገባሁም።**
**5የክፉዎችን ማኅበር ጠላሁ፥**
**ከዝንጉዎችም ጋር አልቀመጥም።**
**6እጆቼን በንጽሕና አጥባለሁ**
**አቤቱ፥ መሠዊያህን እዞራለሁ፥**
**7የምስጋናን ድምፅ እሰማ ዘንድ፥**
**ተአምራትህንም ሁሉ እነግር ዘንድ።**

**26፡1-7** ይህ አንጓ የሚያስረግጠው የመዝሙረኛውን መሻት ነው፣ በያህዌ እንዲፈረድለት። እሱ በአንዳንድ ክፉ ነገሮች ተከስሷል፣ ጣዖት አምልኮ ሊሆን በሚችል።
1. ፍረድልኝ – ቢዲቢ 1047፣ ኬቢ1022፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 7:8፤ 17:2-3፤ 35:24፤ 43:1፤ ያህዌ ሕዝቡን ይፈትናል፣ ኤር. 11:20፤ 12:3፤ 20:12፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 11:4ለ ላይ
2. ፍተነኝ – ቢዲቢ 103፣ ኬቢ 119፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 139:23
3. ሐሳቤን መርምር – ቢዲቢ 650፣ ኬቢ 707፣ *ፒይል ተተኳሪ*፣ መዝ. 7:9፤ ሐሳብ ("ኩላሊቶች") እና ልብ ለሙሉ አካል ፈሊጦች ናቸው (ማለትም፣ አስተሳሰብ፣ ሐሳብ፣ ድርጊቶች)

ደራሲው ከዚያም ለምን ሊፈረድለት እንደሚገባ ምክንያቶቹን ይዘረዝራል።
1. በየውሃቴ ሄጃለሁና – ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ዝኪ. 26:3ለ እና 26:11ሀ፤ ኢዮብ 4:6፤ መዝ. 7:8፤ 25:21፤ 41:12፤ 78:72፤ 101:2፤ ምሳ. 2:7፤ 19:1፤ 20:7፤ 28:6
2. ባለመናወጥ በያህዌ ታምኛለሁ – ሁለቱን ግሦች ተገንዘብ።
   ሀ. መታመን – ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል* PERFECT፣ መዝ. 13:5፤ 52:8፤ ይህ የተመቻቸ ሁኔታ ነው
   ለ. ያለመናወጥ – ቢዲቢ 588፣ ኬቢ 609፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ እሱም በሂደት ላይ ያለ መሻት (ዕብ. 10:23)፤ ተመሳሳይ ምናብ መዝ. 5:8 እና 18:36 ላይ ይከሰታል
3. በእውነትህ ተራምጃለሁና – ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ *ሂትፒይል* የተጠናቀቀ ከዋው ጋር፤ እዚህጋ እውነት ማለት ታማኝነት ነው፣ ዶክትሪን ሳይሆን

4. ከዝንጉዎች ጋር አልቀመጥም – ቢዲቢ 442፣ ኬቢ 444፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 1:1 (ይህ የሚያመለክተው ጣዖት አምላኪነትን ነው፣ ኒዶቴ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 54)
5. ከከንቱዎች ጋር አልተራመድኩም – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
6. የክፉዎችን ማኅበር ጠላሁ – ቢዲቢ 971፣ ኬቢ 1338፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 31:6፤ 139:21
7. ከክፉ ጋር አልተቀመጥኩም – ቢዲቢ 442፣ ኬቢ 444፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
8. እጆቼን በንጽሕና አጥባለሁ – ቢዲቢ 934፣ ኬቢ 1220፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 73:13፤ ዘኁ. 8 እና 9 የአምልኮ ድርጊቶች ናቸው፣ በብሔራዊ አምልኮ ሁነቶች ላይ የሚከናወኑ (ዘዳ. 21:6)
9. በመሠዊያህ እዞራለሁ – ቢዲቢ 685፣ ኬቢ 738፣ *ፖል* ተጓዳኛዊ፣ ይህ የሚያመለክተው አንድ ዓይነት የአምልኮ ሽብሸባ ወይም ዝማሜ ነው፣ ኢያ. 6:3-15፤ መዝ. 43:3-4፤ 48:12
10. ተአምራትህን ሁሉ እናገራለሁ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9:1 ላይ)
    ሀ. ከፍ ባለ ድምጽ መዘመር – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ሂፊል* ያልተወሰነ አወቃቀር
    ለ. ማወጅ – ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765፣ *ፒይል* ያልተወሰነ አወቃቀር፣ መዝ. 9:1፤ 40:5፤ 75:1

በተጠናቀቁትና ባልተጠናቀቁት መካከል ያለውን ልዩነቶች ተገንዘብ። ጊዜ የዕብራይስጥ ግሥ ክፍል እንዳላይደለ አስታውስ፣ የተጠናቀቀ ወይም በሂደት ላይ ያለ ድርጊት ብቻ።

▣ የታማኝ ተከታዮች ጠላቶች ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳላቸው ተገንዘብ።

1. የሚያስቱ ሰዎች (ማለትም፣ ጣዖት አምላኪዎች፣ የማይረቡ፣ ቢዲቢ 996፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 24:4 ላይ)
2. አስመሳዮች (ማለትም፣ ግብዞች፣ ቢዲቢ 761፣ ኬቢ 824፣ *ኒፋል* ቦዝ አንቀጽ)
3. የክፉ አድራጊ ማኅበር (ቢዲቢ 949፣ ኬቢ 1269፣ *ሂፊል* አንቀጽ)
4. ክፉ (ቢዲቢ 957)

ደግሞም የመዝሙረኛው አዎንታዊ ድርጊቶችን ሁሉ መረዳት የሚቻለው በእርሱ ጠላቶች እንደማይደረጉ ነው። እሱ ንጹሕ ነው እናም ፍርድን ይጠይቃል። እነርሱ በደለኞች ናቸው እናም ኩነኔ ይገባቸዋል።

ለጠላቶቹ የገላጭ ቃላት ዝርዝር (መዝ. 1:5፤ 5:10፤ 15:2-5) በቀጣዩ አንጓ እየተስፋፋ ይሄዳል።

5. ኃጢአተኞች (ቢዲቢ 308)
6. ደም አፍሳሾች (ቢዲቢ 60 አወቃቀር ቢዲቢ 196፣ መዝ. 5:6፤ 55:23፤ 139:19)
7. ክፉ አሳቢዎች (ቢዲቢ 273፣ መዝ. 37:7)፣ AB ይህ ጣዖታትን እንደሚያመለክት ሐሳብ አለ (ገጽ. 163)
8. መማለጃ ይቀበላሉ (ቢዲቢ 1005)፣ ዘጸ. 23:8፤ ዘዳ. 16:19፤ መዝ. 15:5

እነዚህ ሰዎች እነማን እንደሆኑ ሊያስደንቅ ይችላል። እነርሱ የኪዳን ሰዎች ናቸውን እምነት-የለሽ ሕይወት የሚኖሩ ወይስ ኪዳን-የለሽ ሕዝቦች ናቸውን ብርሃን የሌላቸው? እግዚአብሔር ይርዳን፣ የሚመስሉት ብርሃን፣ እውነት፣ እና መገለጥ ያላቸውን ሰዎች ነው፣ ነገር ግን እሱን ላለመቀበል የመረጡ!

**26፡3 "ቸርነት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 5፡7 ላይ።

**26፡5 "የክፉዎች ማኅበር"** "ማኅበር" የሚለው ቃል (*ቃሃል፣* ቢዲቢ 874) የብኪ ዳራ ያለው ነው፣ በብኪ ለቤተ ክርስቲያን መጠሪያ፣ *ኢክሌሲያ* ("የተጠሩት፣" ማለትም፣ ቤተ ክርስቲያን) እሱም በLXX ጥቅም ላይ የዋለው *ቃሃል*ን ለመተርጎም ነው።

ሐሳቡ ሁለት ዓይነት ማኅበራት መኖራቸው ነው (ማቴ. 7:13-14)

1. የእግዚአብሔር ታማኝ ሕዝቦች – መዝ. 22:22፣25፤ 35:18፤ 40:9፣10፤ 89:5፤ 107:32፤ 149:1
2. ክፉ አድራጊዎች (ጣዖት አምላኪዎች፣ መዝ. 31:6)

***መዝሙር ፡ 26፡8-12***

**8አቤቱ፥ የቤትህን ስፍራ**
**የክብርህንም ማደሪያ ቦታ ወደድሁ።**
**9ከኃጢአተኞች ጋር ነፍሴን፥**
**ከደም ሰዎችም ጋር ሕይወቴን አታጥፋ።**
**10በእጃቸው ተንኰል አለባቸው፥**
**ቀኛቸውም መማለጃ ተሞልታለች።**
**11እኔ ግን በየውሃቴ ሄጃለሁ**
**አድነኝ ማረኝም።**
**12እግሮቼ በቅንነት ቆመዋልና አቤቱ፥**
**በማኅበር አመሰግንሃለሁ።**

**26፡8-12** ይህ አንጓ ቁ. 1-7 ያይ ያለውን ሐሳብ ትይዩ ያደርገዋል። መዝሙረኛው እንደገና የእርሱን መልካም ነገሮች ይዘረዝራል፣ ለተቀባይነቱ፣ እንዲሁም የጠላቶቹን ድርጊት/ሐሳብ፣ ተቀባይነት ላለማግኘታቸው።

የመዝሙረኛው መልካም ነገሮች

1. *መቅደስህን ወደድኩ* – ቢዲቢ 12፣ ኬቢ 17፣ *ቃሉ* PERFECT
2. በየውሃቴ ተራምጃለሁ – ቢዲቢ 1070፣ ዝክ. 26:1
3. እግሮቼ በተስተካከለ ስፍራ ቆመዋል (መዝ. 27:11)። ይህ ግልጽ ለሆነ መንገድ ዘይቤ ነው፣የተስተካከለ የያህዌ የኪዳን መንገድ፣ መዝ. 119:105

መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይጠይቃል፣ ለእርሱ እንዲያደርግለት፣ በክፉ ላይ ከሚያደርገው በተለየ መልኩ።

1. ነፍሴን ከኃጢአተኞች ጋር አትውሰድ (ማለትም፣ "መሰብሰብ፣" ቢዲቢ 62፣ ኬቢ 74፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ። ይህ ግሥ በጥሬው ጥቅም ላይ የዋለው ለ "መኸር" ነው (ኢሳ. 62:9)። እሱም ለሞት ነው ጥቅም ላይ እየዋለ የመጣው (መሳ. 2:10፤ 2 ነገ. 22:20፤ 2 ዜና. 34:28)።
2. ነፍሴን ከደም ሰዎች ጋር አትውሰድ

እነዚህ ሰዎች የሚታወቁት በደም አፍሳሽነት፣ በክፉ አሳቢነት፣ እና መማለጃ በመቀበል ነው። ጥርት ብሎ ግልጽ የሆነ የሕይወት ስልት ልዩነት አለ፣ በታማኝ ተከታይ እና በእምነተ-ቢስ እስራኤላውያን መካከል፣ እነርሱም የአምልኮ ድርጊትን የሚያደርጉና በአምልኮ ሥርዓት የሚሳተፉ ነገር ግን የሕይወት ስልት ውጤት የሌላቸው (ማቴ. 7:15-27)!

## ልዩ ርዕስ፡- ክህደት (አፌስቴሚይ)

ይህ *አፊስቴሚይ* የተባለው የግሪክ ቃል ሰፊ የሆነ የትርጉም መስክ አለው፡፡ የእንግሊዝኛው አፖስታሲ/ክህደት ከዚህ ቃል ቢወጣም የእግሊዝኛው ቃል አጠቃቀም በዘመናዊው አንባቢዎች ላይ ጥላቻን አሳድሯል፡፡ አውድ እንደተለመደው ቅድመ ማብራሪያ እንዳይደረግ በመከላከል ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

ይህ ቃል የሁለት ቃላት ጥምር ሲሆን እነሱም *አፖ* የሚለው መስተዋድድ ትርጉሙ «ከ» ወይም «ከ...ወደ...» እና *ሂሰትሚይ* የሚለው «መቀመጥ፣» «መቆም፣» ወይም «መወሰን» ማለት ነው፡፡ የሚከተሉትን (ሥነ መለኮታዊ ያልሆኑ) አጠቃቀሞችን ልብ ይበሉ፡-

1. በአካል ማስወገድ
   ሀ. ከቤተ መቅደስ፣ ሉቃስ 2÷37
   ለ. ከቤት፣ ማር.13÷34
   ሐ. ከሰው፣ ማር.12÷:12፤14÷50፤የሐዋ.5÷38
   መ. ከማንኛውም ነገር፣ ማቴ.19÷27፣29
2. በፖለቲካ ማስወገድ፣ የሐዋ.5÷37
3. ከግንኙነት ማስወገድ፣ የሐዋ.5÷38፤15÷38፤19÷9፤22÷29
4. በህግ ማስወገድ (ፍቺ)፣ ዘዳ.24÷1፣3 (LXX) እና አ.ኪ. ማቴ.5÷31፤19÷6፤ማር.10÷4፤1ኛ ቆሮ.7÷11
5. እዳን ማስወገድ፣ ማቴ.18÷24
6. ግድ አለመሰኘትን በመተው ማሳይት፣ ማቴ.4÷209፤22÷27፤ዮሐንስ 4÷28፤16÷32
7. ግድ መሰኘትን ባለመተው ማሳየት፣ ዮሐንስ 8÷29፤14÷18
8. መፍቀድ፣ ማቴ.13÷30፤19÷14፤ማር.14÷6፤ሉቃስ 13÷8

ግሡ ደግሞ በሥነ መለኮታዊ ትርጉሙ ሰፊ አግልግሎት አለው፡-

1. ኃጢያትን በመደምሰ፣ይቅር በማለት፣ነጻ ማድረግ፣ ዘፀ.32÷32 (LXX)፤ዘሑ.14÷19፤ ኢዮብ 42÷10 እና አ.ኪ. ማቴ.6÷12፣14-15፤ ማር.11÷25-26
2. ከኃጢያት በመጠበቅ፣2ኛ ጢሞ.2÷19
3. በመራቅ ግዴለሽ መሆን
   ሀ. ሕግ፣ ማቴ.23÷23፤የሐዋ.21÷21
   ለ.እምነት፣ ሕዝ.20÷8 (LXX)፤ሉቃስ 8÷13፤2ኛ ተሰ.2÷3፤1ኛ ጢሞ.4÷1፤ዕብ.2÷13

ዘመናዊ አማኞች ብዙ የአ.ኪ. ጸሐፊዎች ፈጽሞ ያላሰቡትን ብዙ ሥነ መለኮታዊ ጥያቄዎችን ጥያቄ ይጠይቃሉ፡፡ ከእንዚህ ጥያቄዎች አንዱ እምነትን ከታማኝነት ከመለየት ዝንባሌ ጋር ይያያዛል፡፡

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ከእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል የነበሩ ሰዎች ነበሩና ጥቂት የሆነ ነገር አለ፡፡

1. ብሉይ ኪዳን
   ሀ. 12ቱን (10) ሰላዮች ሪፖርት የሰሙ፣ ዘሑ.14 (ዕብ.3÷16-19)
   ለ. ቆሬ፣ ዘሑ. 16
   ሐ. የኤሊ ልጆች፣ 1ኛ ሳሙ. 2፣4
   መ. ሳኦል፣ 1ኛ ሳሙ. 11-13
   ሠ. የሐሰት ነብያት (ምሳሌዎች)
      1. ዘዳ.13÷1-5፤18÷19-22 (የሐሰት ነብያትን የማወቂያ መንገዶች)
      2. ኤርምያስ 28
      3. ሕዝቅኤል 13÷1-7
   ረ. ሐሰተኛ ሴት ነብያት
      1. ሕዝቅኤል 13÷17
      2. ነህምያ 6÷14

ሰ. የእስራኤል ክፉ መሪዎች (ምስላዎች)

1. ኤርምያስ 5÷30-31፤8÷1-2፤23÷1-4
2. ሕዝቅኤል 22÷23-31
3. ሚኪያስ 3÷5-12

2. አዲስ ኪዳን

ሀ. ይህ የግሪክ ቃል ቃል በቃል *አፖስታሲዝ* ነው፡፡ ከሁለተኛ ምፃት በፊት ስለክፉና ሐሰተኛ ትምህርቶች መጠንከር ሁለቱም ብሉይ እና አዲስ ኪዳኖች ያረጋግጣሉ (ማቴ.24÷24፤ማር.13÷22፤የሐዋ.20÷29፣30፤2ኛተሰ.2÷9-12፤2ኛ ጢሞ.4÷4)፡፡ ይህ የግሪክ ቃል በማቴዎስ 13፤ማርቆስ 4፤ እና ሉቃስ 8 ላይ ያለውን ኢየሱስ ስለ መሬት(አፈር) የተናገረው ምሳሌ ሊያንጸባርቅ ይችላል፡፡ እነዚህ የሐሰት አስተማሪዎች ክርስቲያኖች አለመሆናቸው ግልጽ ነው፤ እነሱ የወጡት ግን ከክርስቲያኖች ውስጥ ነው (የሐዋ.20÷29-30፤ 1ኛ ዮሐ.2÷19)፤ ስለሆነም እነርሱ ያልበሰሉ አማኞችን ማባበልና መማረክ ይችላሉ (ዕብ.3÷12)፡፡

ሥነ መለኮታዎ ጥያቄዎችን የሚጠይቁ ሐሰተኛ መምህራን ወይስ ይልቁን አማኞች? ይህን ጥያቄ ለመመለስ አስቸጋሪ ነው፤ ምክንያቱም በአጥቢያ ቤተክርስቲያን ውስጥ ሐሰተኛ መምህራን ነበሩና (1ኛ ዮሐ.2÷18-19)፡፡ ብዙ ጊዜ ቤተ እምነታዊ ወይም ሥነ መለኮታዊ ልማዳችን ይህንን ጥያቄ ያለ ግልጽ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ይመልሳል (ጥቅሶችን ከአውዳቸው ገንጥሎ አውጥቶ ለአሳባቸው ድጋፍ መረጃ ለማድረግ ከሚሞክሩት በስተቀር)፡፡

ለ. ግልጽ የሐሰት እምነት

1. ይሁዳ፣ ዮሐ.17÷12
2. ስምዖን የሐዋ.8
3. በማቴ.7÷13-23 ላይ የተገለጹት
4. በማቴ.13፤ ማር.4፤ሉቃስ 8 ላይ የተገለጹት
5. በዮሐንስ 8÷31-59 ላይ ያሉት አይሁዳውያን
6. አሌክሳንደር እና ሄሜኔዮስ፣ 1ኛ ጢሚ.1÷19-20
7. በ1ኛ ጢሞቲዎስ 6÷21 ላይ የገለጹት፡፡
8. ሄሜኒዎስ እና ፊሊጦስ፣ 2ኛ ጢሞ.2÷16-18
9. ዴማስ፣ 2ኛ ጢሞ.4÷10
10. የሐሰት መምህራን፣ 2ኛ ጴጥ.2÷19-22፤ ይሁዳ ቁ.22-19
11. የክርስቶስ ተቃዋሚ 1ኛ ዮሐ. 2÷18-19

ሐ. ፍሬ አልባ እምነት

1. 1ኛ ቆሮንጦስ 3÷10-15
2. 2ኛ ጴጥሮስ 1÷8-11

አልፎ አልፎ ስለእነዚህ ጥቅሶች እናስባለን፤ ምክንያቱም የተቀናጀ ሥነ መለኮታችን (ካልቪኒዝም፣አርሚኒያኒዝም፣ወ.ዘ.ተ) በምግዚትነት የሚጠቀሙባቸው መልሶች ስለሆኑ ነው፡፡ ይህንን ርዕስ ስለአመጣሁ ፈጥናችሁ አትፍረዱብኝ፡፡ እኔ ግድ የሚለኝ ትክክለኛ የሥነ ፍታቴ አኪያሂድ ነው፡፡ መጽሐፍ ቅዱስ ለእኛ እንዲናገር ማድረግ አለብን እንጂ ወደ ዘመኑ የኃይማኖት አስተሳሰቦች ስብስብ ውስጥ ልናስገባው አይገባም፡፡ ይህ የሚያሳዝንና የሚያስደነግጥ ነው፤ ምክንያቱም አብዛኛው ሥነ መለኮታችን ቤተእምነታዊ፣ ባህላዊ፣ ግንኙነታዊ (ወላጆች፣ጓደኞች፣መጋቢዎች) ነው እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አይደለም፡፡ ጥቂቶች በእግዚአብሔር ሕዝብ ውስጥ የነበሩ የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ አለመሆን ዞረዋል (ለምሳ. ሮሜ.9÷6)፡፡

**26፡8** ይህ ዘይቤ (ምስል ከሳች) የሚያመለክተው የምድረ-በዳውን ማደርያ ድንኳን ነው (ዘጸአት 25-31፣ 36-40)፣ ኋላ ላይ ግን ሞሪያ ተራራ ላይ ያለውን የኢየሩሳሌም መቅደስ መጥቀስ ጀመረ። እሱም ያህዌ በሕዝቡ መካከል የሚኖርበት ነበር (ማለትም፣ በኪሩቤል ክንፎች መካከል፣ ከኪዳኑ ታቦት በላይ፣ በቅድስተ ቅዱሳን)። ታማኝ ተከታዮች በያህዌ መገኛ ለመሆን ይናፍቃሉ (መዝ. 23:6፤ 27:4-5)።

ቁጥር 6 ደግሞ የማደርያውን ድንኳን/መቅደስ ነው የሚያመለክተው (መዝ. 24:3-4)።

**26፡11** ምንም እንኳ መዝሙረኛው ንጹሕ እንደሆነ ቢያምንም፣ ያህዌ ንጹሕና ቅዱስ መሆኑን ሰዎች ሁሉ አለመሆናቸውን ያውቃል (ኢሳ. 53:6፤ ሮሜ. 1:18-3:18)። አንዱ ወደ ያህዌ ኅብረት በቀረበ ቁጥር፣ የግል ኃጢአትን መጠንቀቁ ይጨምራል (ማለትም፣ መግደፍ እና መፈጸም) እውነታ ይሆናል። መዝሙር 19፡11-14 ይህንን እውነት በደንብ ይገልጻል።

**26፡11**ለ ከእነዚህ ነገሮች የተነሣ ያህዌን ይጠይቃል

1. እንዲቤዠው – ቢዲቢ 804፣ ኬቢ 911፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 19:14
2. እንዲራራለት – ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 25:16

ያህዌ እንደሚፈርድለት ያምናል፣ ስለዚህም ያህዌን ይባርካል

1. በዝማሬ፣ መዝ. 26፡7
2. በምስክርነት፣ 26፡7
3. በባርኮት፣ 26፡12 (ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ ፔይል ያልተጠናቀቀ)

**26፡12 “ማኅበራት”** ኤምቲ የብዙ ቁጥር ነው ነገር ግን እሱ የግርማው ብዙነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል። አአመት፣ አእት፣ የተእመቅ የነጠላ ቁጥር ነው ያላቸው። አእት መጽሐፍ ቅዱስ የብዙ ቁጥሩን “አምላኪዎቹን” እንዲጠቅስ ያደርገዋል (ኖክስ ትርጉም)። የብዙ ቁጥሩ መልክ የሚከሰተው እዚህ እና መዝ. 68፡26 ላይ ብቻ ነው።

▣ **“ጌታን እባርካለሁ”** ይህ የሚያመለክተው አንዱ በያህዌ እምነቱን፣ መታመኑን፣ ተስፋውን፣ እና ታማኝነቱን በይፋ የሚያስታውቅበት ነው (ሮሜ. 10፡9-13)፣ በአምልኮ ስፍራ ሊሆን ይችላል።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ያህዌ ሐሳብንና ልብን እንዴት ይመረምራል?
2. ቁጥር 6 ደራሲው ካህን መሆኑን ያመለክታልን?
3. “ተአምራት” የሚለውን ቃል ግለጽ (ቁ. 7)።
4. ቁጥር 12ሀን በራስህ ቃላት ግለጽ።

## መዝሙር 27
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| መዝሙር ለፍርሃት-የለሽ እምነት በአምላክ ላይ<br><br>ኤምቲ መግቢያ የዳዊት መዝሙር | ይፋዊ የእምነት መግለጫ | የመሰጠት ድርጊት እና የመታደግ ጸሎት (የመታመን መዝሙር) | የምስጋና ጸሎት | ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ወዳጅነት ፍርሃት የለም |
| 27:1-3 | 27:1-3 | 27:1 | 27:1 | 27:1 |
| | | 27:2 | 27:2-3 | 27:2 |
| | | 27:3 | | 27:3 |
| 27:4-6 | 27:4-5 | 27:4 | 27:4-6 | 27:4 |
| | | 27:5 | | 27:5 |
| | 27:6 | 27:6 | | 27:6 |
| | | | | 27:6ሐ |
| 27:7-10 | 27:7-10 | 27:7-9ሀ | 27:7-9ሀ | 27:7-9ሀ |
| | | 27:9ለ-10 | 27:9ለ-10 | 27:9ለ-10 |
| 27:11-14 | 27:11-13 | 27:11-12 | 27:11-12 | 27:11-12 |
| | | 27:13-14 | 27:13-14 | 27:13-14 |
| | 27:14 | | | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መግለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. የመዝሙር 26:8፣12፤ መዝ. 27:4፤ እና መዝ. 28:2 ጭብጥ በእግዚአብሔር ቤት ስለ መሆን መሆኑ (ማለትም፣ የማደሪያ ድንኳን ወይም መቅደስ) እነዚህ መዝሙራት አንድ ላይ የመሆናቸው ምክንያት ይሆናል። መዝሙር 27 ቀጣይነት ያለውና ፍጻሜው ነው "ሳይናወጡ በእግዚአብሔር ስለ መታመን"፣ የመዝሙር 26:1 ጭብጥ።

ለ. ይህ መዝሙር ያማረ ትይዩነት አለው።

ሐ. ማንም በርግጠኝነት አያውቅም፣ የደንቡን መስፈርት አልያም ግለሰቡ(ቦቹ) የተካተቱበትን፣ ዝማሬውን ለማዋቀር፣ እንደምናውቀው (እናም ይልቁንም፣ ሙሉውን ብኪ)። እሱ የእምነት ቅድመ-ግምት ነው፣ ማለትም መንፈስ አዘጋጁንና የማሰባሰቡን ሂደት መምራቱ፣ እሱ ቅዱስ ቃሉን እንደ ጻፈ።

# የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 27፡1-3**

**[1]እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው**
**የሚያስፈራኝ ማን ነው?**
**እግዚአብሔር የሕይወቴ መታመኛዋ ነው**
**የሚያስደነግጠኝ ማን ነው?**
**[2]ክፉዎች፥ አስጨናቂዎቼ ጠላቶቼም፥ *ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ* በቀረቡ ጊዜ፥**
**እነርሱ ተሰናከሉና ወደቁ።**
**[3]ሠራዊትም ቢሰፍርብኝ**
**ልቤ አይፈራም**
**ሰልፍም ቢነሣብኝ**
**በዚህ እተማመናለሁ።**

**27፡1-3** *ይህ መዝሙር ባሕርዩ ለመዘሙረኛው ያህዌ ምን እንደሆነ ነው።*

1. ብርሃን — ቢዲቢ 21፣ ማለትም፣ ይህ ሊያመለክት የሚችለው፡
   ሀ. *መመሪያ* — ምሳ. 6፡23
   ለ. *መሪ* — መዝ. 43፡3
   ሐ. የያህዌ መገኘት — መዝ. 4:6፤ 44:3፤ 89:15
   መ. ሕይወት እና ጠቀሜታ – ኢዮብ 33:28፤ መዝ. 36:10፤ ሚኪያስ 7:8፣ ዩቢኤስ የማስታወሻ መጽሐፍ ገጽ 261
   የ "ብርሃን" ጽንሰ-ሐሳብ ብርቱ ምስያ ነው፣ በጥንታዊው ዓለም። ጨለማ ይፈራል፣ ብርሃን ግን በረከት ነው። እግዚአብሔር እንደ ብርሃን ምናብ በርካታ ፍችዎች ይኖሩታል (ኢሳ. 60:1፣19-20፤ ሚክያስ 7:8፤ እና ዮሐንስ 8:12)።
2. ደኅንነት – ቢዲቢ 447፣ ይህ ሊያመለክት የሚችለው
   ሀ. ደኅንነት – መዝ. 12:6፤ ኢዮብ 5:4፣11
   ለ. መጠበቅ – መዝ. 50:23፤ 69:14፤ 85:7፣9
   ሐ. ዐለት. . . – መዝ. 95:1
   መ. ቀንድ. . . – መዝ. 18:3
3. መጠጊያ – ቢዲቢ 731 (ማለትም፣ የደኅንነት ስፍራ፣ መዝ. 28:8፤ 31:2-3፤ 37:39-40፤ 2 ሳሙ. 22:31-32)

"የመሆን" ግሥ ቁጥር 1፣ ስንኝ 1 እና 3 ላይ የለም። ሌሎቹ ግሦች ያልተጠናቀቁ ናቸው (እንደ ቁ. 3) እሱም በሂደት ላይ ስላለ ድርጊት የሚናገር። ተቃርኖውን ተገንዘብ፣ የክፉ አድራጊዎች/ተቃዋሚዎች/ጠላቶች አቋም ቁጥር 2 ላይ። የእነርሱ አቋም (የተጠናቀቁዎች) ተቀምጧል። እነርሱ ተሰናክለዋል ወድቀዋልም። ያልተጠናቀቁት ግሦች ቁጥር 3 ላይ ይቀጥላሉ። ሕይወት የራሷ ፈተና፣ ችግሮች፣ ገጠመኞች አሏት፣ እግዚአብሔር ግን ዘወትር ከእኛ ጋር እና ለእኛ ነው!

ታማኝ አገልጋዮች ምን ያደርጋሉ፣ በሕይወት ልምምዳቸው አኳያ፣ በወደቀው ዓለም?

1. አይፈሩም፣ ቁ. 1፣3 (ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*)
2. አይደነግጡም፣ ቁ. 1 (ቢዲቢ 808፣ ኬቢ 922፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*፣ መዝ. 118:6፤ ሮሜ. 8:31)
3. ይተማመናሉ፣ ቁ. 3 (ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል የድርጊት ቦዝ አንቀጽ*)

እውነተኛ እምነት ከእግዚአብሔር ጋር የግል ግንኙነት ነው፣ አዲስ ርዕዮተ-ዓለም፣ አዲስ የሕይወት ስልት (ሮሜ. 8፡31-39)! ይህ ሁሉ ይቻላል ከእግዚአብሔር ባሕርይና መገለጥ የተነሣ። እሱ ከእኛ ጋር እና ለእኛ ነው፣ እናም የየዕለቱ ግላዊ ግንኙነት ከእኛ ጋር እንዲኖረው ይሻል፣ በወደቀው ዓለም፣ ከኃጢአተኛ ሰዎች ጋር እንኳ ቢሆን!

**27፡2** *ተቀናቃኞችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን ቃላት ተገንዘብ።*

1. ክፉ አድራጊዎች፣ ቁ. 2 – ቢዲቢ 949፣ ኬቢ 1269፣ *ሂፊል ቦዝ አንቀጽ*
2. ተቃዋሚዎች፣ ቁ. 2፣12 – ቢዲቢ 865 III
3. ጠላቶች፣ ቁ. 2፣6 – ቢዲቢ 33፣ ኬቢ 38፣ *ቃል ቦዝ አንቀጽ*

እነርሱ "ተሰናክለዋል" "ወድቀዋልም" (ኤር. 50:32)። ሁለቱም *ቃል* የተጠናቀቁ ናቸው። የእነርሱ ዕጣ-ፈንታና ፍርድ ቀደም ብለው እንደሆኑ ይታያሉ! ፍጻሜአቸው ርግጠኛ ነው!

▣ ***"ሥጋዬን ይበሉ ዘንድ"*** አእት "ሊገድሉኝ" የሚል አለው፣ እናም ይህ የዘይቤው ኃይል ነው (መዝ. 14፡4)። እሱም ክፉ አድራጊዎች እንደ ምድረ-በዳ አውሬ እንዲሠሩ የሚያመለክት!

የተመት የሚለው፣ ፍችው "ስም ማጥፋት" ነው (ማለትም፣ "ሐሜታ፣" በዳን. 3፡8 ላይ በመመሥረት)፣ አየተመት ባብዛኛው ጥሬአዊ ትርጉም ይጠቀማል።

**23፡7** ይህ ቁጥር በጽኑ የሚያመለክተው መዝሙረኛው ንጉሥ መሆኑን ነው። የመዝሙር 1-41 ዐውደ-ጽሑፍ የሚገልጸው ዳዊት መሆኑን ነው።

በ "ሠራዊት" (ׂצבא ፣ ቢ.ዲ.ቢ 334) እና "ሰፈር" (חנה ፣ ቢ.ዲ.ቢ 333) መካከል ያለውን የቃላት ጨዋታ ተገንዘብ። እንደዚህ ዓይነቶቹ የቃላት ጨዋታዎች በዕብራይስጥ ቅኔ ላይ ዘወትር ይከሰታሉ።

---

**መዝሙር ፡ 27፡4-6**

**4እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እርስዋንም እሻለሁ**
**በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፥**
**እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ፥**
**መቅደሱንም እመለከት ዘንድ።**
**5በመከራዬ ቀን በድንኳኑ ሰውሮኛልና፥**
**በድንኳኑም መሸሸጊያ ሸሽጎኛልና፥**
**በዓለት ላይ ከፍ ከፍ አድርጎኛልና።**
**6እነሆ፥ አሁን በዙሪያ ባሉ በጠላቶቼ ላይ ራሴን ከፍ ከፍ አደረገ**
**በድንኳኑም የእልልታ መሥዋዕትን ሠዋሁ፥**
**ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ እዘምርለትማለሁ።**

---

**27፡4-6** መዝሙረኛው ተለጣጣቂ የጸሎት ጥያቄዎችን ይዘረዝራል። የተጠናቁትን እና ያልተጠናቀቁትን ግሦች ትይዩነት ተገንዘብ።

1. "ለመንኩት" – ቢ.ዲ.ቢ 981፣ K 1371፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ድርጊትን ይጠቅሳል የተጠናቀቀ
2. "እሻለሁ" – ቢ.ዲ.ቢ 134፣ ኬቢ 152፣ *ፔል* ያልተጠናቀቀ፣ ቀጣይነት ያለውን የተጠናከረ የጸሎት ሕይወት ያመለክታል

መዝሙርን ለመተርጎም ማስታወስ የሚኖርብን እነዚህ ጥያቄዎች ለሁለት ተግባራት እንደሚያገለግሉ ነው።

1. እነርሱ ልብንና ሐሳብን ያንጸባርቃሉ (ማለትም፣ አዲስ ርዕዮተ-ዓለም፣ ሕዝ. 36፡22-38) የታማኝ ተከታይን
2. እነርሱም ይቃረናሉ፣ እንዲሁም የሐሰተኛ ተከታዮችን ልብና ሐሳብ በግልጽ ይገልጣሉ

የእግዚአብሔርን መሪዎች የሚቃወሙ እግዚአብሔርን ይቃወማሉ! የሚታየው ብቀላ አይደለም፣ ነገር ግን ፍርድ እና የያህዌ ባሕርይ መገለጥ ነው!

**27፡4** የተጠናከሩትን ጥያቄዎች ተገንዘብ።

1. እኖር ዘንድ (*ቃል* ያልተወሰነ አወቃቀር) በጌታ ቤት በሕይወት ዘመኔ ሁሉ (መዝ. 23፡6)
2. እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም (ቃል ያልተጠናቀቀ አወቃቀር፣ ዘወትር በነቢይ ራዕይ ጥቅም ላይ የሚውል፣ ቢ.ዲ.ቢ 302) አይ ዘንድ፥ (ከታች ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)
3. መቅደሱንም እመለከት ዘንድ (ፔል ያልተጠናቀቀ አወቃቀር)

▣
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**
**አየተመት፣ ጄፒኤስኦኤ፣**

| | | |
|---|---|---|
| | **የተእመቅ** | **"ውበት"** |
| | **አአመመቅ ኅዳግ** | **"ደስ የሚያሰኝ"** |
| **LXX** | | **"አስደሳችነት"** |
| **አእቅ** | | **"መልካምነት** |
| **አኢመቅ** | | **"አስደሳችነት"** |

የዕብራይስጡ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ 653) በመሠረቱ ፍችው "አስደሳች፣" "ደስ የሚያሰኝ" ነው። ስሙ በአብዛኛው በምሳሌ ጥቅም ላይ ይውላል፣ እናም በርካታ የተለያዩ ነገሮችን ይገልጻል። በመቅደስ ዐውደ-ጽሑፍ የእግዚአብሔርን ራዕይ ወይም ከሕይወት በኋላን ሊገልጽ ይችላል። እሱም ከ"መልካምነት" ጋር ትይዩ ነው (ቢ.ዲ.ቢ 375) ቁጥር 13 ላይ፣ እሱም ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ፍጹም መቼትን (ስፍራ) ይገልጻል።

እዚህጋ የዚህ ቃል በምሳሌ ላይ አጠቃቀም ናሙና አለ።

1. ስም – ምሳ. 3:17፤ 15:26፤ 16:21
2. ቅጽል – ምሳ. 22:18፤ 23:8፤ 24:4
3. ግሥ – ምሳ. 2:10፤ 9:17፤ 24:25

**27፡5** የጸሎቱ ውጤቶች፡

1. ያህዌ ይሸሽገዋል (ቢ.ዲ.ቢ 860፣ ኬቢ 1049፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ) በመቅደሱ (መዝ. 76:2) በመከራው ቀን።
2. ያህዌ ይደብቀዋል (ቢ.ዲ.ቢ 711፣ ኬቢ 771፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ) በድንኳኑ ምሥጢራዊ ስፍራ።
3. ያህዌ ከፍ ያደርገዋል (ቢ.ዲ.ቢ 926፣ ኬቢ 1202፣ *ፖለል* ያልተጠናቀቀ) በዓለቱ ላይ (ማለትም፣ ያህዌ ራሱ)።

◘ እኔን ይደንቀኛል፣ የድሮዎቹ አይሁድ ይሄንን ቁጥር ቀድመው ቢጠቅሱት
1. መቅደሱ ቢወድቅ በባቢሎን፣ ግብፅ፣ አዲሲቷ-ባቢሎን
2. አንቲከስ IV ኢፒፋነስ (175-164 ቅ.ል.ክ) መቅደሱን ሲያውክ
3. ሮማውያን መቅደሱን ሲወርሩ፣ በቲቶ ሥር (70 ዓ.ም)

ማስታወስ የሚኖርብን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተስፋዎች ተጽዕኖ የሚኖራቸው
1. ለታማኝ ተከታዮች
2. በእግዚአብሔር ተለቅ ባለ ዓላማው አኳያ በታሪክ ላይ ብቻ ነው

**27፡6** ያህዌ ይህን በመሰለ አስደናቂ መንገድ ለመዝሙረኛው ጥያቄዎች ምላሽ ስለ ሰጠ (ማለትም፣ "በጠላቶቼ ላይ ራሴን ከፍ አደረገ")
1. እሱ መሥዋዕት ያቀርባል፣ በደስታ ጩኸት ("የደስታ ጩኸት መሥዋዕት"፤ ይህን የመሰሉ ቁጥሮች የሚያመለክቱት በአይሁድ ጥቅም ላይ ይውል የነበረውን የንግግር መሥዋዕት ነው፣ ከቤተ መቅደሳቸው መፍረስ በኋላ፣ ዓመታዊውን መሥዋዕት ለማስመሰል፣ ከዛን በኋላ የማይቻለውን)
2. እሱ ለያህዌ ምስጋና ይዘምራል

ሦስት ተደጋጋሚ ግሦች እዚህ ቁጥር ይገኛሉ። መዘሙረኛው ያምናል፣ በያህዌ መገኛ እንደሚሆን (ማለትም፣ መቅደስ)።
1. መሥዋዕት አቀርባለሁ – ቢዲቢ 256፣ ኬቢ 261፣ ቃል
2. እዘምራለሁ – ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ ቃል
3. ምስጋና እዘምራለሁ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ፔል

**መዝሙር ፡ 27፡7-10**

**7አቤቱ፥ ወደ አንተ የጮኽሁትን ቃሌን ስማኝ።**
**ማረኝና አድምጠኝ።**
**8አንተ ፊቴን እሹት ባልህ ጊዜ።**
**አቤቱ፥ ፊትህን እሻለሁ ልቤ አንተን አለ።**
**9ፊትህን ከእኔ አትሰውር፥**
**ተቈጥተህ ከባሪያህ ፈቀቅ አትበል**
**ረዳት ሁነኝ፥**
**አትጣለኝም፥**
**የመድኃኒቴም አምላክ ሆይ፥ አትተውኝ።**
**10አባቴና እናቴ ትተውኛልና፥**
**እግዚአብሔር ግን ተቀበለኝ።**

**27፡7-10** መዝሙር ላይ ዘወትር፣ የተለዩ አንጓዎች የቀደሙትን አንጓዎች አጽንዖት ወይም ጭብጥ ይደግማሉ። ይህም ሊብራራ ይችላል፣ እንደ
1. ሆን ብሎ የተደረገ ትይዩነት ሌላው ደረጃ
2. የአዘጋጅነት ሂደት፣ እዚያም
   ሀ. ቃላት
   ለ. ጭብጦች
   ሐ. ሁኔታ (ድባብ)
   መ. ድርጊቶች

እነርሱም በድምጽ፣ በፍች፣ ወይም በሥነ-መለኮት ተመሳሳይ ይሆናሉ፣ አንድ ላይ ይመደባሉ፣ በኋለኞቹ አዘጋጆች/አጠናቃሪዎች።

**27፡7 "ስማ... ጩኸት"** የመጀመሪያው ቃል ተተኳሪ ነው (ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570)፣ መዝሙር ላይ እጅግ የተለመደ፣ እግዚአብሔርን እንደመለመን። ሁለተኛው ግሥ "ጩኸት" (ቢዲቢ 894፣ ኬቢ 1128፣ ቃል ያልተጠናቀቀ)፣ ደግሞ ጸሎትን ይጠቅሳል።

ይህ ቁጥር የቁጥር 4ን አትኩሮት ይደግማል።
የጸሎት ጥያቄው ዐውድ
1. ማረኝ – ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334፣ ቃል ተተኳሪ
2. መልስልኝ – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ ቃል ተተኳሪ

**27፡8** አአመመቅ እና አኪጀት መግቢያ ሐረግ በኢታሊክስ እንዳላቸው ተገንዘብ (ማለትም፣ "አንተ ባልህ ጊዜ")፣ እሱም የዕብራይስጥ ጽሑፍ ክፍል እንዳልሆነ የሚያመለክት። አየተመት እና አኢመቅ ትርጉሞች፣ ተናጋሪው መዝሙረኛው እንደሆነ ነው የሚገምቱት።
"መፈለግ" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 134፣ ኬቢ 152) ተደግሟል
1. በመጀመሪያ መግቢያው ላይ ቃል ተተኳሪ (የብዙ)

2. *ሁለተኛ ፔል ያልተጠናቀቀ (ነጠላ፣ የመግቢያው ግሥ፣ የቁ. 8 ደግሞ ነጠላ ነው)*
*እነዚህ እየወከሉ ያሉት በያህዌ እና በመዝሙረኛው መካከል ያለውን ንግግር ነው። አንደኛው ይጣራል፣ ሌለኛው በተገቢ ሁኔታ መልስ ይሰጣል። "መፈለግ" የሚለው ግሥ የሚገልጸው የግላዊ ግንኙነት ጥሪን ነው (መዝ. 24፡6፤ ዘዳ. 4፡29)፣ ይኸውም አምልኮና መታዘዝን የሚገልጽ። በዚህ መዝሙር፣ በጸሎት ላይ አጽንዖት በመስጠቱ ሳቢያ፣ ከቁ. 4 እና 7 ጋር ትይዩ ሊሆን ይችላል።*

▣ ***"ፊት"*** *ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ለቀረበ ግላዊ ግንኙነት (መዝ. 24፡6)፣ እዚያም "መፈለግ" እና "ፊት" አብረው የሚከሰቱበት።*

**27፡9** *ተለጣጣቂ የሆኑ ተጽዕኗዊ ግሦች አሉ፣ መዝሙረኛው ያህዌን እንዳያደርግ የሚጠይቀውን ነገሮች የሚያመለክቱ።*

1. *ፊትህን ከእኔ አትሰውር – ቢዲቢ 711፣ ኬቢ 771፣ ሂፊል ተጽዕኗዊ፣ መዝ. 69:17፤ 102:2፤ 143:7*
2. *ተቆጥተህ ከባርያህ ፈቀቅ አትበል – ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ ሂፊል ተጽዕኗዊ*
3. *አትጣለኝ– ቢዲቢ 643፣ ኬቢ 693፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 94:14፣ ታማኝ ተከታይነታቸውን እስካላቆሙ ድረስ (ኤር. 12:7)*
4. *አትተወኝ – ቢዲቢ 736፣ ኬቢ 806፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*

*በእነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ የተካተቱትን ግላዊ ነገሮች ተገንዘብ!*

**27:10**

| | |
|---|---|
| ***አአመመቅ*** | ***"ለ"*** |
| ***አኪጀት*** | ***"መቼ"*** |
| ***አየተመት*** | ***"እንደ"*** |
| ***አእቅ*** | ***"ሊሆን የሚችል"*** |
| ***አኢመቅ፣ ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ*** | ***"እንኳ"*** |
| ***አእት መጽሐፍ ቅዱስ*** | ***"ቢሆንም"*** |

*የመግቢያው ተውሳከ ግሥ* (ቢዲቢ 471-475) *ሰፋ ያለ የፍች መስክ አለው። ዐውድ ብቻ ነው ፍችውን የሚወስነው። ይህ ዐውድ ግልጽ የሆነ ትርጉም እንዳልያዘ ገሀድ ነው።*

▣ **"አባቴና እናቴ ትተውኛልና፥"** *ይህ ተመሳሳይ የሆነ ግሥ ነው፣ 27፡9 ላይ ጥቅም ላይ የዋለው። ምንም እንኳ የዚህ ሐረግ ትርጓሜ ግልጽ ባይሆንም፣ ፍችው ግልጽ ነው። አንድ የሰው የቅርብ ጓደኛ ወይም ቤተሰብ ሊተው ይችላል፣ ነገር ግን ኪዳናዊው አምላክ ፈጽሞ አይተውም (ዘዳ. 31:6፤ ኢያ. 1:5፤ ኢሳ. 49:15፤ ዕብ. 13:5)!*

*ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 266) እንደሚጠቅሰው አእት፣ አእመቅ፣ ኢመቅ ቁጥሩን የሚወስዱት እንደ ንድፈ-ሐሳባዊ ገለጻ ዓይነት ነው፣ ጠንካራ ጽሑፋዊ ነጥብ ለማስቀመጥ፣ ርግጠኛ መተው ሳይሆን።*

*አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ይህ የያህዌን ተስፋ የሚያንጸባርቅ ከሆነ፣ ለዳዊትና ለዘሩ የሰጠውን፣ 2 ሳሙኤል 7 ላይ። ቁጥር 13 ከ2 ሳሙ. 7፡27 ጋር ሊዛመድ ይችላል።*

***መዝሙር ፡ 27፡11-14***

**[11]አቤቱ፥ መንገድህን አስተምረኝ፥**
**ስለ ጠላቶቼም**
**በቀና መንገድ ምራኝ።**
**[12]የሐሰት ምስክሮችና**
**ዓመፀኞች ተነሥተውብኛልና**
**ለጠላቶቼ ፈቃድ አትስጠኝ።**
**[13]የእግዚአብሔርን ቸርነት**
**በሕያዋን ምድር አይ ዘንድ አምናለሁ።**
**[14]እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ**
**በርታ፥ ልብህም ይጽና**
**እግዚአብሔርን ተስፋ አድርግ።**

**27፡11-14** *ይህ አንጓ የሚጀምረው በተጨማሪ የጸሎት ጥያቄ ነው (ቁ. 11-12)፣ ወደ እምነት ምስክርነት የሚያመራ (ቁ. 13)፣ እናም በመልካም ምክር ያጠቃልላል (ቁ. 14)።*

**27፡11-12** *የጸሎት ጥያቄዎቹ*

1. *መንገድህን አስተምረኝ – ቢዲቢ 434፣ ኬቢ 436፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ መዝ. 25:4-5፤ 86:11*

2. በቀና መንገድ ምራኝ – ቢዲቢ 634፣ ኬቢ 685፣ *ቃል ተተኳሪ፣* ዘዳ. 5:32-33፤ 31:29፤ መዝ. 5:8፤ 26:12፤ 139:24፤ ይህ የብኪ ዳራ ያለው ነው፣ ቤተ-ክርስቲያን "መንገድ፣" ተብላ የምትጠራበት ሐዋ. 9:2፤ 18:25፤ 19:9፣23፤ 22:4፤ 24:14፣ 22፤ ዮሐንስ 14:6

3. ለጠላቶቼ ፍቃድ አትስጠኝ – ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ መዝሙረኛው ሁለት ምክንያቶችን ይሰጣል፣ ስለ ጸሎቱ፣ በዚህ አንጓ ላይ።

1. ስለ ጠላቶቼ ("አድብተው የሚጠባበቁኝ")፣ ቁ. 11
2. የሐሰት ምስክሮች በእኔ ላይ ስለተነሡ፣ ቁ. 12

**27:13** ይህ ቁጥር የመዝሙረኛውን እምነት ይገልጻል ("አምናለሁ" – ቢዲቢ 52፣ ኬቢ 63፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ) እና ርዕዮተ-ዓለም። እሱ እንዳለ ያምናል

1. ፍትሕ በዚህ ሕይወት፣ ከያህዌ ባሕርይ የተነሣ
2. ቀጣይ ሕይወት ከያህዌ ጋር በሕያዋን ምድር (ኢዮብ 14:7-12፣13-14፤ 19:25-27፤ መዝ. 16:10፤ 49:15፤ 73:24፤ 116:8-9፤ 142:5፤ ኢሳ. 25:8፤ 26:19፤ 38:11)

**27:14** ከመዝሙረኛው እምነትና ርዕዮተ-ዓለም የተነሣ ሌሎችን ይመክራል

1. ጌታን እንዲጠብቁ – ቢዲቢ 875፣ ኬቢ 1082፣ *ፒል ተተኳሪ፣* መዝ. 25:3፤ 37:34፤ 40:1፤ 62:1፣5፤ 130:5፤ ምሳ. 20:22፤ ኢሳ. 8:17፤ 25:9፤ 33:2
2. ጠንካራ እንዲሆኑ – ቢዲቢ 304፣ ኬቢ 302፣ *ቃል ተተኳሪ፣* መዝ. 31:24
3. ልባችሁ ይጽና – ቢዲቢ 54፣ ኬቢ 65፣ *ሂፊል* ተጽዕኗዊ
4. ጌታን እንዲጠብቁ – ቢዲቢ ከቁ. 1 ጋር ተመሳሳይ

አንዳንድ ሊቃውንት (ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 439) ቁ. 14 ተመልከት እንደ

1. ራስን መምከር
2. ካህናዊ መገለጥ፣ በመቅደስ የተሰጠ

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "ፍርሃት" እንዴት ቁልፍ ቃል ይሆናል፣ በመጀመሪያው አንጓ?
2. ቁጥር 2 እና መዝሙር 23፡6 የድምጽ ተመሳሳይነታቸው፣ ይህ ምናባዊ አንድምታው ምንድነው?
3. ቁጥር 4-6 ስለ ማደርያው ድንኳን ነው ወይስ ስለ መቅደስ?
4. ቁጥር 9 እጅግ አስቸጋሪነቱ ለምንድነው፣ ኪዳናዊው አምላክ ተከታዮቹን ተዋቸውን?
5. ቁጥር 10 የሚለው ምንድነው? በጥሬው ነው ወይስ ዘይቤአዊ?

# መዝሙር 28
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጆት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| የዕርዳታ ጸሎትና የመልሱ ምስጋና<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር። | ለተመለሰ ጸሎት ምስጋና | ከግል ጠላቶች የመታደግ ጸሎት (ሰቆቃ) | የዕርዳታ ጸሎት | ልመናና ምስጋና ማቅረብ |
| 28:1-5 | 28:1-2 | 28:1-2 | 28:1-3 | 28:1 |
| | | | | 28:2 |
| | 28:3-5 | 28:3-5 | | 28:3 |
| | | | 28:4-5 | 28:4 |
| | | | | 28:5 |
| 28:6-9 | 28:6-7 | 28:6-7 | 28:6-7 | 28:6 |
| | | | | 28:7 |
| | 28:8-9 | 28:8-9 | 28:8-9 | 28:8-9 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 28፡1-5**

1አቤቱ፥ ወደ አንተ እጠራለሁ
ዝም ብትለኝ
ወደ ጓድጓድ እንደሚወርዱት እንዳልመስል፥
አንተ አምላኬ፥ ዝም አትበለኝ።
2ወደ መቅደስህ ማደሪያ እጄን ባነሣሁ ጊዜ፥
ወደ አንተ የጮኽሁትን የልመናዬን ቃል ስማ።
3ከኃጥአንና ከክፉ አድራጊዎች ጋር ነፍሴን አትውሰዳት
ክፋትም በልባቸው እያለ
ከባልንጀራቸው ጋር ሰላም ከሚናገሩት ጋር አትጣለኝ።
4እንደ ሥራቸው እንደ አካሄዳቸውም ክፋት ስጣቸው
እንደ እጃቸውም ሥራ ስጣቸው
ፍዳቸውን ወደ ራሳቸው መልስ።
5ወደ እግዚአብሔር ሥራ ወደ እጆቹም አደራረግ አላሰቡምና
ያፈርሳቸዋል እንጂ አይሠራቸውም።

**28፡1-5** አንጓዎቹን እንዴት መከፋፈል እንደሚገባ በዚህ መዝሙር ላይ አለመግባባት አለ (የዚህን ምዕራፍ የፊት ገጽ ተመልከት)። አአመመቅ ቁ. 1-5፣ 6-9 አለው፣ ስለዚህ እሱን እጠቀማለሁ። የመጀመሪያው አንጓ ሰቆቃ ነው ሁለተኛው ምስጋና የማቅረብ የመዝሙር።

*መዝሙረኛው ይጸልያል*

1. ሲጸልይ ያህዌ እንዲሰማው
2. ያህዌ እንደ ክፉዎች እንዳያወጣው

ቁጥር 4 ላይ ሦስት ተተኳሪዎችን ይጠቀማል፣ እግዚአብሔር በክፉዎች ላይ ማድረግ የሚኖርበትን ለመግለጽ።

1. ስጣቸው (ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ *ቃል ተተኳሪ*) እንደ *ሥራቸው* (ኢዮብ 34:11፤ መዝ. 62:12፤ ምሳ. 24:12፤ መክ. 12:14፤ ኤር. 17:10፤ 32:19፤ ማቴ. 16:27፤ 25:31-46፤ ሮሜ. 2:6፤ 14:12፤ 1 ቆሮ. 3:8፤ 2 ቆሮ. 5:10፤ ገላ. 6:7-10፤ 2 ጢሞ. 4:14፤ 1 ጴጥ. 1:17፤ ራዕ. 2:23፤ 20:12፤ 22:12)
2. እንደ አካሄዳቸውም ክፋት ስጣቸው (ግሥ ይሆናል ተብሎ የሚገመተው ከ ቁ. 1 ነው)
3. ስጣቸው (እንደ ቁ. 1 ተመሳሳይ ግሥ) እንደ እጃቸውም *ሥራ* ("የእጃቸው *ሥራ*")
4. ክፈላቸው (ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ *ሂፊል ተተኳሪ*) የፍዳ ክፍያ ("ብድራት፣" ቢዲቢ 168)

**28፡1 "ዐለቴ"** ይህ ምናባዊ (ምስላዊ) የሚናገረው ዘላለማዊ፣ ብርቱ፣ ጽኑዕ፣ መጠጊያ ነው (መዝ. 18፡2 ላይ ሙሉውን ማስታወሻ ተመልከት)።

▣ **"አታድርግ..."** እነዚህ ሁለት ያልተጠናቀቁ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋሉት።

1. ስማ – ዝም አትበል፣ ቢዲቢ 361 II፣ መዝ. 35:22፤ 39:12፤ 83:1፤ 109:1 (ከ"ዝምታ" ጋር ትይዩ ቢዲቢ 364)
2. ቁ. 2 – አትጣለኝ፣ ቢዲቢ 604 (ማለትም፣ እንደ እንስሳ ወይም የጦር እስረኛ ሊሆን ይችላል)

▣ **"ጉድጓድ"** ቃሉ (ቢዲቢ 92፣ መዝ. 88:4፤ 143:7፤ ምሳ. 28:17) የሲዖል ተመሳሳይ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው? መዝ. 1:5 ላይ። እሱም ሊዛመድ የሚችለው

1. የተቆፈረ መቃብር (ኢሳ. 14:9፤ ሕዝ. 32:25)
2. የኮረብታ ጉድጓድ ለቀብር
3. ወደ ሲዖል የሚሄድ ደጅ (መዝ. 30:4፤ ምሳ. 1:12፤ ኢሳ. 14:15፤ 38:18፤ ሕዝ. 26:20)

**28፡2 "ወደ መቅደስህ ማደሪያ እጄን ባነሣሁ ጊዜ፥"** ይህ የእጅ ምልክት በርካታ ፍችዎች አሉት።

1. የመባረክ ድርጊት፣ ከመሥዋዕት በኋላ፣ በካህን — ሌዋ. 9፡22 (ማለትም፣ አንዳንድ መሥዋዕቶች ወደ ያህዌ ከፍ ይደረጋሉ)
2. በአምላኪው በኩል የሚከናወን ድርጊት፣ ከዕጣን መሥዋዕት በኋላ — መዝ. 141፡2
3. ወደ መቅደስ እጅ የማንሣት ምልክት — መዝ. 134፡2
4. የጸሎት አካላዊ ድርጊት፣ እጆች ይነሣሉ፣ ዘጸ. 9:29 (ሙሴ)፤ 1 ነገ. 8:22 (ሰሎሞን)፤ ሰቆ. 2:19፤ 3:41 (እስራኤል)፤ ሉቃስ 24:50 (ኢየሱስ)፤ 1 ጢሞ. 2:8 (አማኞች)
5. እጅ የማንሣት ምልክት ለምስጋና፣ አምልኮ፣ ወይም ለአደባባይ ምስክርነት – መዝ. 63:4
6. የያህዌን ኃይል ማሳያ መንገድ፣ በትሩ በሙሴ እጅ ላይ ከፍ ባለ ጊዜ (ዘጸ. 17:8-12)

እዚህ ፍችው ተምሳሌትነቱ ንጹሕ ሕይወት ነው (1 ጢሞ. 2፡8)፣ ለእግዚአበሔር ክፍት የሆነ ሕይወት፣ መሻቱንም ከእግዚአብሔር ለመቀበል የሚገነዘብ (አሉታዊ አጠቃቀሙን ተመልከት መዝ. 44፡20 ላይ)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ወደ ቅዱሱ ማደርያህ"** |
| **አአመመቅ ኅዳግ** | |
| **አየተመት የግርጌ ማስታወሻ** | **"ወደ ውስጠኛው ስፍራ"** |
| **አኢመቅ** | **"ቅድስተ ቅዱሳን"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ወደ ውስጠኛው መቅደስህ"** |
| **LXX** | **"ችሎት"** |
| **የተእመቅ** | **"መቅደስ"** |

ይህ የዕብራይስጥ ቃል (ቢዲቢ 184 I) በመሠረቱ ፍችው "የጀርባ ክፍል፣" "ውስጠኛ" ነው። 1 ነገሥት 6:16፣19፣20፣21፣22፣23፣31፤ 7:49፤ 8:6፣8 የሚያመለክተው ቅድስት ቅዱሳንን ነው (ዘጸ. 26:31-35)፣ እዚያም የኪዳኑ ታቦት በሰሎሞን ትላልቅ ኪሩቤል መካከል የቆመበት።

ታማኝ ተከታዮች በብሉይ ኪዳን በመቅደሱ ፊት ይሆናሉ (1 ነገሥት 8፣ የሰሎሞን ታላቁ ጸሎት፣ በመቅደስ ምርቃት ላይ) በሚጸልዩበት ጊዜ፣ ምክንያቱም ያህዌ የሚያድረው እዚያ ስለነበር፣ በኪሩቤል ክንፎች መካከል። ሰማይና ምድር የሚገናኙት እዚያ ነበር። የኪዳኑ ታቦት የያህዌ የእግሩ መረገጫ ነበር።

ሆኖም፣ በአዲስ ኪዳን፣ እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ አለ (ዮሐንስ 4፡20-24)። አዲሱ መቅደስ ኢየሱስ ነው (ዮሐንስ 2፡19፣ 21)!

**28፡3፣5 "ምክንያት. . ."** ቁጥር 3 እና 5 የክፉውን ድርጊቶችና አዝማሚያዎች ይዘረዝራል (ማለትም፣ ተግባራዊ ኢ-አማኒዎች)።

1. ክፉን የሚሠሩ፣ ቁ. 3
2. ለባልንጀራቸው ሰላምን የሚናገሩ ነገር ግን በልባቸው ክፉ የሚያስቡ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 4፡7 ላይ)
3. የእግዚአብሔርን ሥራዎች የማይመለከቱ፣ ቁ. 5 (የእግዚአብሔር ሰዎች "መመልከት" ይኖርባቸዋል፣ እሱ ማን እንደሆነ፣ ባደረገው ነገር፣ ዘዳ. 32፡7፤ መዝ. 107፡43፤ ኤር. 2፡10፤ ሆሴ. 14፡9)
4. የእግዚአብሔርን ሥራዎች የማይመለከቱ (ትይዩ)፣ ቁ. 5፣ ኢሳ. 5፡12

**28፡5** የቁጥር 5 የመጨረሻው ስንኝ የሚነግረን እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግባቸው ነው (ከኤር. 1፡10 ጋር አነጻጽር)።

1. ያፈርሳቸዋል – ቢዲቢ 248፣ ኬቢ 256፣ ቃል ያልተጠናቀቀ፣ ቁ. 5
2. አይሠራቸውም – ቢዲቢ 124፣ ኬቢ 139፣ ቃል ያልተጠናቀቀ፣ አሉታዊ፣ ቁ. 5

የቁጥር 5 ሦስቱ ያልተጠናቀቁዎች የሚገልጹት የክፉውን ቀጣይነት ያለው ድርጊት ነው። የሕይወታቸው ባሕርይ እግዚአብሔርን መተውና ሌሎችን መጉዳት ነው፣ ስለዚህ፣ የእግዚአብሔርም ፍርድ ይቀጥላል (ማለትም፣ የሚደጋገም ጥፋት፣ ኢሳ. 6፡9-10፤ ኤር. 1፡10)።

**መዝሙር ፡ 28፡6-9**

**[6]የልመናዬን ቃል ሰምቶኛልና**
**እግዚአብሔር ይመስገን።**
**[7]እግዚአብሔር ኃይሌና ጋሻዬ ነው**
**ልቤ በእርሱ ታመነ እኔም ተረዳሁ**
**ሥጋዬም ደስ ይለዋል፥**
**ፈቅጄም አመሰግነዋለሁ።**
**[8]እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኃይላቸው ነው፥**
**ለቀባውም የመድኃኒቱ መታመኛ ነው።**
**[9]ሕዝብህን አድን፥ ርስትህንም ባርክ ጠብቃቸው፥**
**ለዘላለሙም ከፍ ከፍ አድርጋቸው።**

**28፡6-9** ሥር-ነቀል የአቅጣጫ ለውጥ ቁጥር 6 ላይ ይከሰታል። ይህ አንጓ ይፈነጥቃል፣ ያህዌ የሚባረክበትን ምክንያት (ቁ. 6ሀ)።

1. ጸሎቱን ሰምቷል
2. እሱ ሁለቱንም ነው፣ ብርታቱና ጋሻው
3. መታመኛው ነው

ቁጥር 8 እና 9 ላይ አትኩሮቱ ይቀየራል፣ ከንጉሡ (ማለትም፣ "ከተቀባው") ወደ ኪዳኑ ሕዝብ። ያህዌ ንጉሡን እንዳዳነ፣ አሁን ደግሞ ሕዝቡን ያድናል! ይህ የነጠላና የብዙ መቀያየር በመዝሙር ላይ የተለመደ ነው።

▣ **"እግዚአብሔር ይመስገን"** ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ መዝሙር ላይ። እሱ በታማኝ ተከታዮቹ ይመሰገናል፣ በብዙ ምክንያቶች፣ ነገር ግን ሁሉም ተመልሰው ይመጣሉ፣ ወደ እሱ እና እሱ ወዳደረገው! ይህ ሐረግ የአምልኮ ደንብ ቀመር ሆኗል (መዝ.18፡46፤ 28፡6፤ 31፡21፤ 41፡13፤ 66፡20፤ 68፡35፤ 72፡18፤ 89፡52፤ 106፡48፤ 119፡12፤ 124፡6፤ 135፡21፤ 144፡1)። እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን!

**28፡7** ቁጥር 3 እና 5 ክፉውን እንደሚገልጹ፣ ቁጥር 7 ታማኝ ተከታይን ይገልጻል።

1. ልቡ በእርሱ ይታመናል – ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 1200፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 112፡7 (ሥነ-መለኮታዊውን ግንኙነት ተገንዘብ፣ በሰዎች እምነት እና በመለኮታዊ መዳን/ደኅንነት መካከል ያለውን መዝ. 22፡4-5፤ 25፡1-3፤ 28፡7፤ 31፡14-15፤ 86፡2፤ ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 646 ላይ ማስታወሻ ተመልከት)
2. እርሱ በእግዚአብሔር ተረድቷል – ቢዲቢ 740፣ ኬቢ 810፣ ኒፋል የተጠናቀቀ
3. ልቡ ተደስቷል – ቢዲቢ 759፣ ኬቢ 831፣ ቃል ያልተጠናቀቀ ከዋው ጋር
4. እሱ በመዝሙር ያመሰግነዋል – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ (የቀጠለ ምስጋና)

ስለ ኤምቲ አልያም LXX አጭር አስተያየት ለመስጠት ያህል። ምናልባት እጅግ ጥንታዊ የዕብራይስጥ ጽሑፍ ሊኖር ይችላል፣ ከሁለቱ ኋላ። ኤምኤስኤስ በዲኤስኤስ አለ፣ ኤምቲን የሚከተል፣ ሌሎችም LXXን የሚከተሉ። ጥንታዊዋ ቤተ ክርስቲያን LXXን ከሞላ ጎደል በብቸኝነት ትጠቀም ነበር። ቁጥር 7 መልካም ምሳሌ ነው፣ ለእነርሱ የተለየ የዕብራይስጥ ጽሑፍ ትርጉም። LXX አለው (ልዩ ርዕስ ተመልከት ኤቢ፣ ገጽ 173 ላይ)

"እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፣ ጠባቂዬም፤ ልቤም እሱን ተስፋ ያደርጋል፣
ረዳት ሆኖኛል፣ ሥጋዬም ይለመልማል፣ ፈቅጄም አመሰግነዋለሁ።"

◘ **"ጋሻ"** መዝ. 3፡3 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

**28፡8 "የእነርሱ"** የዩቢኤስ ጽሑፍ ፕሮጀክት "የሕዝቡ" የሚል አለው፣ ደረጃ "ሐ" (ማለትም፣ ምክንያታዊ ጥርጣሬ)።

1. የእነርሱ – למו (ኤኪጀት፣ ጄፒኤስኦኤ)
2. የሕዝቡ – לעמו (ኤየተመት፣ አእቅ፣ ኤኢመቅ፣ የተእመቅ)

ሴፕቱዋጂንት ቁ.2ን ይጠቀማል፣ አንዳንድ የዕብራይስጥ የእጅ ጽሑፎች እንደሚያደርጉት። በግልጽ ሁኔታ፣ አንድ የዕብራይስጥ ፊደል ከኤምቲ ላይ ተገድፏል።

◘ **"ለቀባውም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሢሕ መዝ. 2፡2 ላይ። ተመሳሳይ አጠቃቀም መዝ. 18፡50 ላይ ተመልከት።

**28፡9** ተለጣጣቂ የሆኑ ተተኳሪዎች ተመልከተዋል፣ በጸሎት ለያህዌ፣ በኪዳኑ ሕዝብ አኳያ እንዲያደርግ እሱን የሚለምን።

1. አድን – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 106:47
2. ባርክ – ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ *ፔል ተተኳሪ*
3. እረኛ – ቢዲቢ 944፣ ኬቢ 1258፣ *ቃል ተተኳሪ* (አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ [ገጽ 765] የሚሰጠው አስተያየት "እረኛ" ከመዝሙር 23 ጋር ይያያዛል፣ እና ምናልባት መዝሙር 23-28 ምልክት ተደርጎበታል፣ የመዝሙራት ስብስብ እንደሆነ፣ በበርካታ የተለመዱ ጭብጦች የተያያዙ)
4. ማንሣት (ማለትም፣ "ከፍ ማድረግ")፣ ፔል ተተኳሪ፣ ኢሳ. 40:11፤ 63:9

በርካታ መዝሙራት በተጠቃለለ አትኩሮት ይዘጋሉ (ማለትም፣ መዝ. 3:8፤ 15:7፤ 25:22፤ 29:11፤ 51:18-19፤ 130:8)።

◘ **"ርስትህ"** ያህዌ የርስት ድርሻ ለአሕዛብ ሁሉ ሰጥቷል (ዘዳ. 32፡9)፣ ነገር ግን የአብርሃም ዘሮች የእርሱ የተለዩ ሕዝቦች ናቸው (ዘጸ. 19:5-6፤ 1 ነገ. 8:51፤ መዝ. 33:12)። እሱም ይሄንን አሳይቷል፣ ተስፋውን በዘጸአት ላይ ከግብፅ በማውጣት (ዘፍ. 15፡12-21)። እሱ ኃይሉንና ፍቅሩን አሳይቷል (ዘዳ. 9፡29)። ሙሴ ያህዌን ለምኗል፣ በኃጢአተኛ ሕዝቡ ላይ እንዳይፈርድ፣ ጣዖት አምላኪ ሕዝቦች ስለማይገነዘቡ (ዘዳ. 9፡26-29)። የእርሱ ሕዝቦች ማለት ለአሕዛብ የእርሱን ባሕርይ እንዲገልጡ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት የመዝሙር 2 መግቢያ ላይ)። ነገር ግን ኃጢአትንና ጣዖት ማምለክን ከቀጠሉ መተው ይኖራል (መዝ. 106:40፤ ሕዝ. 36:22-23)።

◘ **"ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም፣ መዝሙር 9፡5 ላይ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የብኪ የሞት አመለካከት ምንድነው?
2. ቁጥር 4 ተመሳሳይ እውነት ነወይ፣ እንደ ገላ. 6፡7?
3. ቁጥር 5ሐ ከኢሳ. 6፡9-10 ወይም ኤር. 1፡10 ጋር ይዛመዳልን?
4. የግለሰቦችን አስተሳሰብና ሁኔታ የሚያንጸባርቁ መዝሙራት የጋራ በሆኑ ተተኳሪዎች ለምን ያጠቃልላሉ?

# መዝሙር 29
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር ድምጽ በማዕበል<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር | ምስጋና ለእግዚአብሔር በቅድስናውና በግርማው | ውዳሴ ለማዕበሉ ጌታ | የጌታ ድምጽ በማዕበሉ | ውዳሴ ለማዕበሉ ጌታ |
| 29:1-2 | 29:1-2 | 29:1-2 | 29:1-2 | 29:1-2 |
| 29:3-9 | 29:3-4 | 29:3-4 | 29:3-4 | 29:3-4 |
| | 29:5-7 | 29:5-6 | 29:5-6 | 29:5-6 |
| | | 29:7-8 | 29:7-9 | 29:7-9ለ |
| | 29:8-9 | | | |
| | | 29:9 | | 29:9ሐ-11 |
| 29:10-11 | 29:10-11 | 29:10-11 | 29:10-11 | |

## የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር ስለ ተፈጥሯዊ መገለጥ ነው (ማለትም፣ እግዚአብሔር ራሱን ይገልጣል፣ ለእያንዳንዱ፣ በፍጥረት በኩል)።
1. መዝሙር 19፡1-6 (የጸጥታ ድምጽ በፍጥረት)
2. ሮሜ 1፡19-23 (የእግዚአብሔር እውቀት ከተፈጥሮ)
3. ሮሜ 2፡14-16 (ውስጣዊ የሞራል ምስክር)

ለ. የመዝሙሩ ምናባዊነት (ምስል ከሳችነት) ለማጠቃለል ተከስቷል
1. የያህዌ ቀውሱን ማሸነፍ፣ በፍጥረት መነሻ ላይ (ማለትም፣ ውኃ፣ ዝከ. 29፡3፣10፣ "ጎርፍ" የሚለው ቃል [ቢዲቢ 550] እዚህና ዘፍጥረት ላይ ብቻ ነው የሚከሰተው ምዕራፍ 6-11)
2. የያህዌ ኃይል በማዕበሉ ላይ (ዝከ. 29:3-9፤ መዝ. 18:7፣15)

ሐ. ያህዌ፣ በአል ሳይሆን፣ ውኃን ያሸንፋል፣ ይቆጣጠራል፣ እናም ይልካል። ብዙ ሊቃውንት በርካቶቹን ተመሳሳዮች መዝግበዋል፣ ከዑጋሪታዊ አፈ-ታሪክና ከሌሎቹ ጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ሥነ-ጽሑፍ ጋር።

መ. ዩቢኤስ የማስታወሻ መጽሐፍ የሚያስረግጠው ይህ መዝሙር መስቀልያ መሆኑን ነው (ገጽ 275)።
1. አራትዮሽ የያህዌ አጠቃቀም፣ ቁጥር 1-2 እና 10-11
2. "ብርታት" (ቢዲቢ 738) ቁ. 1 እና 11 ላይ

3. ውኖች ተመልክተዋል፣ ቁ. 3 እና 10 ላይ
4. የያህዌ ግርማ ተጠቅሷል፣ ቁ. 4 እና 10 ላይ
5. ዛፎች ተጠቅሰዋል፣ ቁ. 5 እና 9 ላይ
6. መልክዓ ምድራዊ ስፍራዎች፣ ቁ. 6 እና 8 ላይ

እዚህ ላይ የእኔ ችግር፣ መስቀልያ እጅግ ጠቃሚውን ሥነ-መለኮታዊ ቃል በመሐል ነው የሚያስቀምጠው፣ ነገር ግን ቁጥር 7 ይህንን ፈርጅ አይገጥምም።

ሠ. ይህ መዝሙር ሊያመለክት የሚችለው
1. የያህዌን መገለጥ ነው፣ በጽኑ ማዕበል ምስያ መጥቶ ሲታይ
2. የሚታመነው ግን ወታደራዊ ድል ነው (ዝኪ. ቁ. 11)

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 29፡1-2**
**1የአምላክ ልጆች ሆይ፥ ለእግዚአብሔር አምጡ።**
**ክብርንና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አምጡ።**
**2የስሙን ክብር ለእግዚአብሔር አምጡ፥**
**በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ።**

**29:1-2 "አምጡ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 396፣ ኬቢ 393፣ *ቃል ተተኳሪ*) ሦስት ጊዜ ተደግሟል። በመሠረቱ ፍችው "ለእግዚአብሔር ክብር ስጡ" ነው (ዘዳ. 32:3)። ይኸው ተመሳሳይ ፈርጅ ደግሞ መዝሙር 96:7-8 እና 1 ዜና. 16:28-29 ላይ አለ።

**29:1**
**አአመመቅ "የብርቱው ልጆች"**
**አኪጀት "እናንተ ብርቱዎች"**
**አየተመት፣ አእቅ "ሰማያዊ ሕላዌዎች"**
**አኢመቅ፣ LXX "የእግዚአብሔር ልጆች"**
**ጀፒኤስአኤ "መለኮታዊ ሕላዌዎች"**
**የተእመቅ "እናንተ መልአካዊ ኃይላት"**

ኤምቲ "የአማልክት ልጆች" የሚል አለው ("የኤሊም ልጆች፣" ቢዲቢ 119 አወቃቀር ቢዲቢ 42)። እሱም መላእክት ያመለክታል (ዘፍ. 6:2 ["የኤሎሂም ልጆች"]፤ መዝ. 103:20-21) ወይም ሰማያዊ የመላእክት ጉባኤ (ዘጸ. 15:11፤ 2 ነገ. 22:19፤ መዝ. 82:1፤ 86:6-8)።

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር ልጆች፣ ከታች ያለውን።

## ልዩ ርዕስ፡ "የእግዚአብሔር ልጆች" በዘፍጥረት 6

ሀ. "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚለውን ሐረግ አገላለጽን በተመለከተ ታላቅ ውዝግብ አለ። ሦስት ዋና ዋና ትርጓሜዎች ነበሩ።

1) ሐረጉ የሚያመለክተው የሴትን መልካም ዘር ነው (ዘፍ. 5፣ በ4፡14 ላይ የሚገኘውን ማስታወሻ ተመልከት)
2) ሐረጉ የሚያመለክተው የመላእክትን ወገን ሕላዌ ነው
3) ሐረጉ የሚያመለክተው የቃየን ዘር የሆኑትን ገዥዎችን ነው (ዘፍ. 4)

ለ. ሐረጉ የሴት የዘር ሐረግ አመላካች ለመሆኑ ማስረጃ

1) የዘፍ. 4 እና 5 ዋነኛው ጽሑፋዊ ዳራ የሚያመለክተው ዐመፀኛው የቃየን ዘር ሐረግና የተመረጠው የሴት ዘር ዘር እድገትን ነው። ስለሆነም፣ ተጓዳኝ ጽሑፋዊ ማስረጃው ወደ መልካሙ የሴት ዘር ሞገስ ያለው ይመስላል
2) ራቢዎች በዚህ አንቀጽ ላይ ባላቸው መረዳት ተከፋፍለዋል። ጥቂቶች ሴትን ያመላክታል ሲሉ (አብዛኞች ግን ለመላእክት ነው)።
3) የብዙ ቁጥር የሆነው ሐረግ "የእግዚአብሔር ልጆች፣" ዘወትር ለመላእክታዊ ሕላዌ ጥቅም ላይ ቢውልም፣ አንዳንዴ ለሰው ልጆች ይጠቀሳል
ሀ. ዘዳ. 14፡1– "የያህዌ ልጆች ያምላካችሁ"
ለ. ዘዳ. 32፡5 – "የሱ ልጆች"
ሐ. ዘጸ. 22፡8-9፤ 21፡6 (ምናልባት ሌዋዊ ዳኛ)
መ. መዝሙር 73፡15 – "የሱ ልጆች"
ሠ. ሆሴዕ 1፡10 – "የሕያው እግዚአብሔር ልጆች"

ሐ. ሐረጉ መልአካዊ ሕላዌን ስለ ማመላከቱ ማስረጃ

1. ይህ በጣም የተለመደው ባህላዊ የአንቀጹ መረዳት ነው። የዘፍጥረት ሰፊው ክፍል ይህንን አተያይ ይደግፈዋል፣ ከተፈጥሮ በላይ የሆነው ክፉ እግዚአብሔርን ለሰው ልጅ ያለውን ፍቃድ በመቃወም ነው (ራቢዎች ከቅናት የተነሣ ነው ይላሉ)
2. የብዙ ቁጥር የሆነው ሐረግ ("የእግዚአብሔር ልጆች") በብኪ በብዛት የተጠቀሰው ለመላእክት ነው
   ሀ. ኢዮብ 1፡6
   ለ. ኢዮብ 2፡1
   ሐ. ኢዮብ 38፡7
   መ. መዝሙር 29፡1
   ሠ. መዝሙር 89፡6፣7
   ረ. ዳንኤል 89፡6
3. አዋልድ መጽሐፍ የሆነው 1ኛ ሄኖክ (ሔኖክ 6፡1-8፡4፤ 12፡4-6፤ 19፡1-3፤ 21፡1-10) እና ጁቢለስ (ኢዮብ 5፡1)፣ እሱም በአኪ ጊዜ በነበሩ አማኞች ዘንድ በጣም የታወቀ ነው፣ በዘፍጥረት አፖክሪፖን ከሙት ባሕል ጥቅሎች፣ እነዚህን የሚተረጉሟቸው እንደ ዐመፀኛ መላእክት ነው
4. የምዕራፍ 6 የወዲያውኑ ጽሑፍ አንድምታው የሚመስለው፣ "ኃያል ሰዎች በድሮ ጊዜ የነበሩ፣ ስማቸው የተጠራ ነበሩ" የሚመጣው ከዚህ ያላግባብ የተደባለቀ የተፈጥሮ ሥርዓት ነው
5. ሴፕቱዋጂንት "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚለውን ሐረግ "የእግዚአብሔር መላእክት" ብሎ ተርጉሞታል
6. 1ኛ ሄኖክ እንዲያውም የሚለው የኖህ የጥፋት ውኃ የመጣው ይሄንን የመላእክት/ሰዎች ኅብረትን፣ እሱም ከያህዌ እና
7. ለፍጥረት ካለው እቅድ ጋር ባላንጣነት ያለውን ለመደምሰስ ነው (1ኛ ሄኖክ 7፡1፤ 15፡1፤ 86፡1)
8. በዩጋሪቲክ ሥነ ጽሑፍ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚያመላክተው የአማልክትን አባላት ነው (አነስተኛ መንፈሳዊ ሕላዌዎች)

መ. የቃየንን የዘር ግንድ ነገሥታትና ገዥዎችን የሚያጣቅሰው ሐረግ ማስረጃ

1. በርካታ ጥንታዊ ትርጉሞች አሉ፣ ይሄንን አተያይ የሚደግፉ
   ሀ. የኦንከሎስ ታርጉም (ሁለተኛ ክፍለ ዘመን ዓ.ም) "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚለውን "የጌቶች ልጆች" በሚል ተርጉሞታል
   ለ. ሲማቸስ (ሁለተኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም) የግሪኩ የብኪ ትርጓሜ፣ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚለውን "የነሥታት ልጆች" በሚል ተርጉሞታል
   ሐ. "ኤሎሄም" የሚለው ቃል ለእስራኤል መሪዎች ይውል ነበር (ዘጸ. 21፡6፤ 22፡8፤ መዝ. 82፡1፣6)፣ አኪት እና አእት መጽሐፍ ቅዱስ ተመልከት
   መ. ኔፌሊም የሚያያዘው ከጊቦሪም ጋር ነው፣ ዘፍ. 6፡4፣ ጊቦሪም ከጊቦር ሲሆን ትርጉሙም "ጽኑዕ ኃያል ሰው፤ ጠንካራ፤ ባለጠግነት ወይም ኃይል፡

   ሠ. ይህ ትርጓሜና የእሱም ማስረጃ የተወሰደው ከ የመጽሐፍ ቅዱስ ጠንካራ አባባሎች ገጽ 106-108 ነው።

ሠ. የሁለቱንም አጠቃቀሞች አራማጆች ታሪካዊ ማስረጃ

1. ሐረጉ የሚያመለክተው ሴቲተስን ነው

| | |
|---|---|
| ሀ. የአሌክሳንደሩ ሲሪል | ሠ. ካልቪን |
| ለ. ቲዮዶርት | ረ. ካይሊ |
| ሐ. አውግስጢኖስ | ሰ. ግሌሰን አርከር |
| መ. ጀሮም | ሸ. ዋትስ |

2. ሐረጉ የሚያጣቅሰው መልአካዊ ሕላዌዎችን ነው

| | | |
|---|---|---|
| ሀ. የሴፕቱዋጂንት ጸሐፊዎች | ሰ. ቴርቱሊያን | ኀ. ኦልፎርድ |
| ለ. ፊሎ | ሸ. ኦሪጅን | ነ. ዌስተርማን |
| ሐ. ጆሴፈስ (አንቲኲቲስ) 1፡3፡1) | ቀ. ሉተር | ኘ. ዌንሃም |
| መ. ጀስቲን ማረታየር | በ. ኢዋልድ | አ. አእት መጽሐፍ ቅዱስ |
| ሠ. ኢሪኒዩስ | ተ. ዴሊዝች | |
| ረ. የአሌክሳንደሪያው ክሌመንት | ቸ. ሄንግስተንበርግ | |

ረ. ዘፍ. 6፡4 ጋ ያሉት "ኔፍታሊሞች" ከ "እግዚአብሔር ልጆች" እና "ከሰው ሴት ልጆች" ዘፍ. 6፡1-2 ጋር እንዴት ይዛመዳሉ?

እነዚህን ንድፈ ሐሳቦች ልብ በል፡
1. እነሱ በጣም ግዙፎች ናቸው (ዘኍ. 13፡33) በመላእክትና በሰው ሴቶች መካከል በተደረገ ግንኙነት።
2. ፈጽመው አይዛመዱም። እነሱ የተጠቀሱት በምድር ላይ ስለመኖራቸው ነው፣ በዘፍ. 6፡1-2 በነበረው ክስተት ጊዜ፣ ከዚያም በኋላ።
3. አር. ኬ. ሃሪሰን *የብሉይ ኪዳን መግቢያ*፣ ገጽ 557፣ የሚከተለው ክሪፕቲክ ጥቅስ አለው፣ "ሁሉንም ዋጋቸው የማይገመተውን የአንትሮፖሎጂአዊ ውስጠቶች ከሆሞሳፒያን ጋር ያላቸውን ግንኙነት፣ እንዲሁም ቅድመ አዳም ዘርያዎች፣ አንቀጹ የያዛቸው፣

እናም ለእነዚህ ሊቃውንት አቋም እንዲሆን፣ ሊጠቀሙበት የሚሹት።" ይህ ለእኔ የሚያመለክተኝ፣ እንዚህን ሁለት ምድቦች የሚመለከት እንደ ተለያዩ የሰው (ሆማኒዱድስ) ምድቦች ነው። ይህ የሚያሳየው ኋለኛው ልዩ ፍጥረት፣ አዳም እና ሔዋንን ነው፣ ግን ደግሞ በዝግመተ ለውጥ እየተሻሻለ የመጣውን ሆሞ ኢረክተስን ነው።

ሰ. ይሄንን አወዛጋቢ ጽሑፍ ራሴ በግሌ እንዴት እንደተረዳሁት ግልጽ ማድረግ ተገቢ ይመስለኛል። አንደኛ፣ ሁላችንንም ላስገነዝብ የምሻው የዘፍጥረት ጽሑፍ አጭርና አሻሚ መሆኑን ነው። የሙሴ የመጀመሪያ አድማጮች የግድ ተጨማሪ ታሪካዊ ውስጠት ሊኖራቸው ትገባል፣ ወይም ሙሴ ሥነ ቃል ወይም የተጻፉ ማስረጃዎችን ከአባቶች ዘመን ወስዶ ሊሆን ይችላል፣ ይህም ራሱ እንኳ ባግባቡ ያልተረዳውን። ይህ ጉዳይ ዋነኛ ሥነ መለኮታዊ ርዕሰ ጉዳይ አይደለም። እኛ ዘወትር ንቁዎች ነን፣ መጽሐፍ ቅዱስ ፍንጫቸውን ብቻ በሰጣቸው፣ ግን አሻሚ በሆኑ ጉዳዮች ላይ። ከእንደዚህ ዓይነቱ ተመሳሳይ የተበጣጠሱ የመጽሐፍ ቅዱስ መረጃዎች ላይ ተንተርሶ የተብራራ ሥነ መለኮትን መገንባት አድካሚ ነው። መረጃው ለእኛ ካስፈለገ፣ እግዚአብሔር ይበልጡን ግልጽ በሆነና በተሟላ መልኩ ሊሰጠን ይችል ነበር። እኔ በግሌ የማምነው፣ መላእክትና ሰዎች ናቸው፣ ምክንያቱም፡

1. በቋሚነት፣ ምንም እንኳ እንዳይካተቱ ባያደርግም፣ "የእግዚአብሔር ልጆች" የሚለው ሐረግ ለመላእክት ነው፣ በብኪ
2. ሴፕቱዋጂንት (የአሌክሳንደሪያ) የሚተረጉመው (በአንደኛው ክፍለ ዘመን ዓ.ም መጨረሻ ላይ) "የእግዚአብሔር ልጆች" እንደ "እግዚአብሔር መላእክት"
3. የአፖካሊፕስ መጽሐፍ 1ኛ ሄኖክ (ወደ 200 ዓ.ዓ የተጻፈ የሚሆን) በጣም የተለየ (ተናጠላዊ) ነው፣ እሱም የሚያመላክተው መላእክትን ነው (ምዕራፍ 6-7)
4. የ2ኛ ጴጥ. 2 እና ይሁዳ፣ ለመላእክት፣ እነሱም ኃጢአት ለሠሩና ተገቢ ማደሪያቸውን ላልጠበቁ ለአንዳንዶች ይሄ ከማቴ. 22፡30 ጋር እንደሚቃረን አውቃለሁ፣ ግን እነዚህ የተለዩ መላእክት በሰማይም ሆነ በምድር አይደሉም፣ ግን በልዩ እስር ቤት ናቸው (ታርታሩስ)።
5. እኔ እንደሚመስለኝ፣ በዘፍ. 1-11 የሚገኙት ሁነቶች በሌሎች ባህሎች የመገኘታቸው ምሥጢር፣ (ማለትም፣ ተመሳሳይ የተፈጥሮ ሐተታዎች፣ ተመሳሳይ የጥፋት ውኃ ሐተታዎች፣ መላእክት ሴቶችን ስለመውሰዳቸው ተመሳሳይ ሐተታ) የሆነው ሰዎች ሁሉ አንድ ላይ በመሆናቸውና፣ በዛን ሰዓት የያህዌ እውቀት ያላቸው በመሆኑ ሲሆን፣ ነገር ግን ከባቢሌል ግንብ መበተን በኋላ ይህ እውቀት በመበላሸቱና ከአንድ በላይ የሆነ አምላክ ወደ ማምለክ በመቀየሩ ነው። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው የግሪክ አፈ ታሪክ ሲሆን፣ እሱም ግማሽ ሰውና/ግማሽ ከተፈጥሮ በላይ የሆኑ ቲታንስ የሚባሉ ግዙፎች፣ በታርታረስ ታስረዋል፣ ይሄው ሁነኛ ስም በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም ላይ የዋለው አንድ ጊዜ ብቻ ነው (2ኛ ጴጥ. 2) ተገቢ ማደሪያቸውን ላልጠበቁ መላእክት ማቆያ ስፍራ። በራቢያዊ ሥነ-መለኮት ሀሳብ በተለያዩ ምድቦች ተከፋፍሏል፣ ለጻድቃን (ገነት) እንዲሁም ለክፉዎች ምድብ (ታርታረስ)።

◘ **"ክብር እና ኃይል"** እነዚህ ሁለት የተለመዱ ቃላት ለያህዌ የሚውሉ ናቸው።
1. ክብር — ቢዲቢ 458
2. ኃይል — ቢዲቢ 738

**29፡2 "ስገዱለት"** ይህ አራተኛው ነው የተለጣጣቂ አራት የመከፈቻ ተተኳሪዎች ("ስገዱ፣" ቢዲቢ 1005፣ ኬቢ 295፣ ሂሽፓል ተተኳሪ)። ይህ ታማኝ ተከታዮች የሚያደርጉት ነው፣ ወደ መቅደሱ በቅዱስ ሥነ-ሥርዓት ሲመጡ። ይህም አለባበስን ብቻ አይደለም የሚያካትተው፣ የኪዳን ታማኝነትን ደግሞ እንጂ።

◘ **"ስሙ"** ይህ ፈሊጣዊ መንገድ ነው፣ ያህዌን ራሱን ለመጥቀሻ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ስም፣ መዝሙር 5፡11-12።

◘

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በተቀደሰ ሥነ-ሥርዓት"** |
| **አኪጀት** | **"በቅድስና ውበት"** |
| **አየተመት፣ አኢመቅ** | **"በቅዱስ ግርማ"** |
| **ጀፒኤስአኤ፣ አአመመቅ ኅዳግ** | **"በቅድስና ግርማዊነት"** |
| **የተእመቅ፣ አእት** | **"በተቀደሰ ድንቅ አለባበስ"** |
| **LXX፣ ፔሺታ** | **"በቅዱስ ችሎቱ"** |

አሻሚው ሐረግ (ቢዲቢ 214 አወቃቀር ቢዲቢ 871) ደግሞ ይከሰታል፣ በሦስት ሌሎች የመቅደስ አምልኮ ዐውዶች ላይ (መዝ. 96፡9፤ 110፡3፤ 1 ዜና. 16፡29)። አእት የግርጌ ማስታወሻ ሦስት ታሳቢ መንገዶችን ያቀርባል፣ ሐረጉን ለመተርጎም።
1. እሱ (ያህዌ) በተከሰተ ጊዜ (ከውኃሪት ሥር፣ አእት፣ ማለትም፣ ያህዌ ራሱ፤ እንግዲያውስ ይህ ከዘጸአት 19-20 መገለጥ ጋር ይመሳሰላል)
2. የአምልኮ አልባሳት (የአሮን አልባሳት በተመሳሳይ መንገድ ነው የተገለጹት፣ ዘጸ. 28፡2 ላይ)
3. በእርሱ ውብ መቅደስ (LXX የሚያንጸባርቅ ይመስላል)

**መዝሙር ፡ 29፡3-9**

**[3]የእግዚአብሔር ድምፅ በውኆች ላይ፥**

የክብር አምላክ አንጐደጐደ፥
እግዚአብሔር በብዙ ውኆች ላይ።
4የእግዚአብሔር ድምፅ በኃይል ነው
የእግዚአብሔር ድምፅ በታላቅ ክብር ነው።
5የእግዚአብሮር ድምፅ ዝግባን ይሰብራል
እግዚአብሔር የሊባኖስን ዝግባ ይቀጠቅጣል።
6እንደ ጥጃ ሊባኖስን፥
አንድ ቀንድ እንዳለው አውሬ ልጅ ስርዮንን ያዘልላቸዋል።
7የእግዚአብሔር ድምፅ የእሳቱን ነበልባል ይቈርጣል።
8የእግዚአብሔር ድምፅ ምድረ በዳውን ያናውጣል፥
እግዚአብሔር የቃዴስን ምድረ በዳ ያናውጣል።
9የእግዚአብሔር ድምፅ ዋላዎችን ያጠነክራቸዋል፥
ጫካዎቹንም ይገልጣል
ሁሉም በመቅደሱ። ምስጋና ይላል።

**29፡3-9** ይህ አንጓ በ "እግዚአብሔር ድምጽ" ተሞልቷል። እሱን ለመመልከት ሁለት መንገዶች ያሉ ይመስላል።

1. ያህዌ ፈጣሪው፣ ዝኪ. ቁ. 3፣10 (ዘፍጥረት 1፤ መዝሙር 93)
2. ያህዌ እውነተኛው ማዕበል አምላክ እና ዝናብ ሰጭ (ዝኪ. ቁ. 3-9፣ ማለትም፣ የበአልን ባለቤትነት በመቃወም)

የያህዌ ድምጽ ባሕርይ የተገለጸበትን መንገድ ተገንዘብ (ቁ. 4-9)።

1. በኃይል (ቢዲቢ 470)
2. በክብር (ተመሳሳይ ሥር፣ ቁ. 2ለ፣ ቢዲቢ 214)
3. ዝግባዎችን ይሰብራል (ግሥ፣ ቢዲቢ 990፣ ኬቢ 1402 ቁ. 5 ላይ ተደግሟል)
4. ሊባኖስንና ስርዮንን (ማለትም፣ አርሞንኤም ተራራ፣ ዘዳ. 3:9) ያዘልላል
5. መብረቅ (መዝ. 18:12፣14) ዛፎችን ያቃጥላል
6. ምድረ-በዳውን ያናውጣል (ግሥ፣ ቢዲቢ 296፣ ኬቢ 297፣ ቁ. 8 ላይ ተደግሟል)
7. ዋላዎችን ያጠነክራቸዋል
8. ጫካዎችንም ይገልጣል (ቢዲቢ 362 I)

ማስታወስ ጠቃሚ የሚሆነው የንግግር ቃል እጅግ ጠቃሚ እና የሚያስፋፋ ነበር፣ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳቦችን በጥንታዊ ዕብራይስጥ።

1. ፍጥረት በንግግር ቃል – Genesis 1
2. የእግዚአብሔር ንግግር ቃል ኃይል – ኢሳ. 14:24፤ 25:1፤ 45:23፤ 46:10፤ 55:11፤ 59:21፤ ማቴ. 24:35
3. መሢሑ "ቃል" ተብሎ ተጠርቷል፣ ዮሐንስ 1:1-5፣14፤ ራዕ. 19:13 ላይ
4. ዳግም የሚመጣው መሢሕ ምናባዊ (ምስል ከሳች) ለአንደበት በሁለት ወገን የተሳለ ሰይፍ – ራዕ. 1:16፤ 2:12

**29፡6 "ሊባኖስ… ስርዮን"** እነዚህ መልክዓ-ምድራዊ ጠቃሾች ናቸው፣ ከከነዓን ከተስፋይቱ ምድር በስተሰሜን። "ስርዮን" የሚለው ቃል ለአርሞንኤም ተራራ ያልተለመደ ነው (ዘዳ. 3፡9)። በዚህ ምክንያትና ግልጽ በሆነው ዐውድ ወይም "ማዕበል" ምስያ፣ በርካታ ዘመናዊ ሊቃውንት ይሄንን መዝሙር የሚመለከቱት፣ በዋነኝነት ለበአል የሆነውን ውዳሴ ዳግም እንደተሠራ ነው (የከነአን የማዕበል ጣዖት)። የራስ ሻምራ ጽሑፎች አብዛኞቹን የተሸፈኑ የብኪ ምናቦች ገልጠዋል፣ በከነዓናውያን አፈ-ታሪክ አኳያ። የዕብራይስጥ ደራስያን ዘወትር የጣዖት አማልክትን መግለጫዎች ይወስዱና ወደ ያህዌ መግለጫዎችና መጠሪያዎች ይለውጧቸዋል። እሱ ብቸኛውና እውነተኛው አምላክ እንደሆነ አውቀዋል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት፣ መዝ. 2፡7 ላይ)።

ለመልካም አጭር ማብራሪያ፣ ለጥንታዊ ሐተታ-ተፈጥሮ አይቪፒ የመጽሐፍ ቅዱስ ምናባዊነት መዝገበ-ቃላት፣ ገጽ 169-174 ተመልከት።

**29፡9ሀ** ተመሳሳይ ግሥ (ቢዲቢ 296፣ ኬቢ 297) "ያናውጣል" በሚል ተተርጉሟል፣ ቁጥር 8 ላይ (ሁለቴ) እነሆ አሁን ጥጃ ስለ መውለድ ጥቅም ላይ ውሏል (ኢዮብ 39፡1) እና ሳራ ስለ መውለዷ፣ ኢሳ. 51፡2 ላይ።

አንዱ ተመሳሳይ ትይዩነትን መጠበቅ ቢሞክር፣ በ29፡9ለ እና 29፡5ለ መካከል፣ እንግዲያውስ "ቀይ ሴት ኢጋዘንን" ("hinds") (ኤምቲ፣ ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል) ወደ "ቡናማ ዋርካ" ("oaks") መቀየር ይኖርበታል (እእት፣ አኢመቅ፣ ተመሳሳይ ተናባቢዎች፣ የአናባቢዎች ለውጥ ብቻ)። ይህም የተደረገው ታሳቢውን ተገላቢጦሻዊ ፈርጅ ለማስቀጠል ከመሞከር ነው።

እእት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 885 ቁ. 21) ማረሚያ አድርጓል፣ "ጫካ"ን ወደ "ሴት የተራራ ፍየል"፣ ተመሳሳይ ትይዩነትን በቁጥር 9ሀ እና 6 መካከል ለማምጣት። ጄፒኤስኦኤ የግርጌ ማስታወሻ አለው፣ "በጎች ቀድመው ይወልዳሉ" እንደ አማራጭ (ቢዲቢ 362 II)።

**29፡9ሐ** የዚህ ድርጊት ሁሉ ማጠቃለያ (ማለትም፣ የኃይለኛው የመብረቅ ነጎድጓድ አካላዊ ውጤት) በመቅደሱ ሁሉም፣ "ምስጋና!" ይላል።

ያህዌ ፈጣሪው የግብርና ምርትን በዝናብ በወቅቱ ይሰጣል። ፈጣሪ ደግሞ መጋቢ ነው! (መልካም አንቀጽን ተመልከት በ"መጋቢነት" ላይ፣ አይቪፒ *የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ምናብ መዝገበ-ቃላት* ገጽ 681-683።)

አኢመቅ ቁ. 9ሐን የቁ. 10-12 መጀመሪያ ያደርገዋል።

**መዝሙር ፡ 29፡10-11**

**[10]እግዚአብሔር የጥፋት ውኃን ሰብስቦአል**
**እግዚአብሔር ለዘላለም ንጉሥ ሆኖ ይቀመጣል።**
**[11]እግዚአብሔር ለሕዝቡ ኃይልን ይሰጣል**
**እግዚአብሔር ሕዝቡን በሰላም ይባርካል።**

**29፡10** "ንጉሥ" የሚለው ቃል ስንኝ 1 ላይ አይደለም፣ ግን ስንኝ 2 ላይ ነው። የጥፋት ውኃ የሚያመለክተው (1) ዘፍጥረት 6-9 (ዘፍ. 6፡17) ወይም (1) የፍጥረት መጀመሪያ (ዘፍ. 1፡2)።

ያህዌ እንደ ንጉሥ የሆነበት ጽንሰ-ሐሳብ ወደ ኋላ ተመልሶ ወደ 1 ሳሙ. 8፡7 ይሄዳል። እሱም የተቀመጠው እንደ ሥነ-መለኮታዊ ማስረገጫ ነው፣ መዝሙር 10፡16 ላይ እና እዚህ። ምናባዊ ምስያው ያህዌ ዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ነው (መዝ. 2፡4፤ 113፡5 እና የኢሳይያስ 6 ምናባዊ ምስያ) ወይም በትረ-መንግሥት ያለው።

▣ ***"ተቀምጧል... ንጉሥ ሆኖ ይቀመጣል"*** "ተቀምጧል" ወይም "በዙፋኑ (ቢዲቢ 442፣ ኬቢ 444) ለዘላለም" የሚለው ግሥ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (ዘጸ. 15፡18፤ መዝ. 9፡7፤ 10፡16፤ 29፡10፤ 66፡7፤ 145፡13፤ 146፡10፤ኤር. 10፡10፤ ሰቆ. 5፡19)።

▣ **"በውኃ ላይ"** መስተጻምሩ የሚያመለክተው

1. በሚናወጡ ውኆች ላይ ያለውን ኃይልና ሥልጣን LXX
2. በሰማይ ያለው ያህዌ ከላይኛው ውኃ በላይ ነው (ማለትም፣ ዝናብ)፣ ከደመናት በላይ (ዘፍ. 1፡6-7፤ መዝ. 148፡4)

"የጥፋት ውኃ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 550) የሚገኘው ዘፍጥረት እና እዚህ መዝሙር 29፡10 ላይ ብቻ ነው።

**29፡11** ያህዌ ንጉሥ በመሆኑ፣ ሕዝቦቹ የተጠበቁ ናቸው። ተስፋዎቹ የተጠበቁ ናቸው። የወደፊት ዓላማው የተጠበቀ ነው!

"በማዕበል" መካከል እንኳ፣ የተፈጥሮ ኃይላት አስከፊ በሚመስሉበት ጊዜ፣ የያህዌ ሕዝቦች ሰላም ናቸው (ማቴ. 8፡23-27፤ 14፡22-33)! ኢየሱስም ይሄንን መለኮታዊ ኃይል ተግባራዊ አድርጎታል፣ በወጀብና በማዕበል ላይ!

# መዝሙር 30
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ከሞት በመዳን ምስጋና ማቅረብ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>"መዝሙር፣ ዝማሬ ለቤት መመረቅ።" የዳዊት መዝሙር። | የተመለሰ ጸሎት ምስጋና | ምስጋና ስለ ፈውስ | ምስጋና የማቅረብ ጸሎት | ከሞት አደጋ መዳን ኋላ ምስጋና ማቅረብ |
| 30:1-5 | | | | |
| | 30:1-3 | 30:1-3 | 30:1-3 | 30:1-3 |
| 30:6-9 | 30:4-7 | 30:4-7 | 30:4-5 | 30:4-5 |
| | | | 30:6-7 | 30:6-7 |
| 30:10-12 | 30:8-10 | 30:8-10 | 30:8-10 | 30:8-9 |
| | | | | 30:10-12 |
| | 30:11-12 | 30:11-12 | 30:11-12 | |

## የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

5. የመጀመሪያው አንቀጽ
6. ሁለተኛው አንቀጽ
7. ሦስተኛው አንቀጽ
8. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

መግቢያው፣ እሱም ኤምቲ ላይ ያለው፣ ዋነኛ አይደለም (ማለትም፣ በዲኤስኤስ መዝሙር አይደለም)። እሱም በግልጽ ኋላ ላይ የተጨመረ ነው (መግቢያ ለመዝሙር 7፣ 60)። እነዚህን መግቢያዎች እንደ ተመስጧዊ አልቀበልም (ግሌአሰን አርከር፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ውዝግቦች ኢንሳይክሎፔዲያ*፣ ገጽ 243 ተመልከት)፣ ስለዚህ፣ በእነርሱ ላይ አስተያየት አልሰጥም።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 30፡1-5**

**ለቤቱ መመረቅ ምስጋና የዳዊት መዝሙር።**
**1 አቤቱ፥ ተቀብለኸኛልና፥**
**ጠላቶቼንም ደስ አላሰኘህብኝምና ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ።**
**2 አቤቱ አምላኬ፥**
**ወደ አንተ ጮኽሁ ምሕረትም አደረግህልኝ።**
**3 አቤቱ፥ ነፍሴን ከሲኦል አወጣሃት፥**

**ወደ ጉድጓድም እንዳልወርድ አዳንኸኝ።**
**[4]ቅዱሳን ሆይ፥ ለእግዚአብሔር ዘምሩ፥**
**ለቅድስናውም መታሰቢያ አመስግኑ።**
**[5]ቍጣው ለጥቂት ጊዜ ነው፥**
**ሞገሱ ግን ለሕይወት ዘመን**
**ልቅሶ ማታ ይመጣል፥**
**ጥዋት ግን ደስታ ይሆናል።**

**30፡1-5** *መዝሙረኛው ያህዌን ያከብራል ያመሰግናልም፣ ከሞት በመዳኑ።*

**30፡1 "አከብርሃለሁ"** ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ. 926፣ ኬቢ. 1202፣ *ፖለል* ያልተጠናቀቀ በኅብራዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ) ሁለት ቀዳሚ ፍችዎች አሉት።

1. ማክበር፣ ማመስገን፣ (እዚህ ለያህዌ)፣ ዘጸ. 15፡2፤ መዝ. 34፡3፤ 99፡5፣9፤ 107፡32፤ 118፡28፤ 145፡1፤ ኢሳ. 25፡1
2. ከፍ ማድረግ (ያህዌን ማመስገን የሚጠቅስ)፣ 2 ሳሙ. 22፡47፤ መዝ. 18፡46፤ 21፡13፤ 46፡10፤ 57፡5፣11

ይህ ምስጋና የተሰጠው ያህዌ ስላደረገ ነው።

1. እሱ ከፍ አድርጓል (ቢዲቢ 194፣ ኬቢ. 222፣ *ፒል* የተጠናቀቀ) መዝሙረኛውን፣ ቁ. 1 (ይህ *ቃል* ጥቅም ላይ የዋለው ከጉድጓድ ውኃ ማውጣትን ነው፣ እናም እሱ በመለኮት ከጉድጓድ መውጣትን የሚጠቅስ ይሆናል ዝከ. 30፡4)።
2. የመዝሙረኛውን ጠላቶች እንዲደሰቱ አላደረገም (ቢዲቢ 33፣ ኬቢ. 38፣ *ቃል* አንቀጽ)፣ መዝ. 25፡2፤ 41፡11.
3. ፈውሶታል (ቢዲቢ 750፣ ኬቢ. 1272፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ ከ*ዋው*)፣ ቁ. 2።
4. ነፍሱን ከሲኦል አውጥቷል (ቢዲቢ 748፣ ኬቢ. 828፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ)፣ ቁ. 3።
5. በሕይወት እንዲኖር አድርጓል (ቢዲቢ 310፣ ኬቢ. 309፣ *ፒል* የተጠናቀቀ)፣ ቁ. 3።

**30፡2 "አቤቱ፣ ጌታዬ አምላኬ"** ይህ ሁለቱ እጅግ የተለመደው የእስራኤል አምላክ መጠሪያ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፣ መዝ. 1፡1 ላይ)።

1. ያህዌ — እግዚአብሔር እንደ አዳኝ፣ ኪዳን አድራጊው አምላክ፣ ዘፍ. 2፡4
2. ኤሎሂም — እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ እና ሕይወትን ሁሉ ሰጭ፣ በዚህ ዓለም ላይ፣ ዝፍ. 1፡1

ይህ መዝሙር እንዴት በዚህ መጠሪያ እንደጀመረ ተገንዘብ (ቁ. 2) እንዲሁም በዚህ መጠሪያ እንደ ፈጸመ (ቁ. 12)። ይህ የተለመደ የዕብራይስጥ የጽሑፍ ስልት ነው (ማለትም፣ ኢንክሉሲዮ (አካታች)።

## ልዩ ርዕስ፡ ፈውስ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነውን፣ ለየዘመናቱ?

1. ፈውስ ዋነኛው የአገልግሎት ገጽታ ነበር፣ ለኢየሱስና ለሐዋርያት?
2. እሱም በቅድሚያ የታሰበው ፍጹም አዲስ የሆነውን መልእክት ለማጽናት ነበር፣ ስለ እግዚአብሔርና ስለ መንግሥቱ።
3. እሱም የእግዚአብሔርን ልብ ያሳያል፣ ለተጎዱ ሰዎች።
4. እግዚአብሔር አልተለወጠም (ሚል. 3፡6) እናም እሱ አሁንም በፍቅር ፈውሱ በኩል ይሠራል።
5. ፈውስ ያልተከናወነባቸው ምሳሌዎች አሉ።
   ሀ. ጳውሎስ፣ 2 ቆሮ. 12፡7-10
   ለ. ጥሮፊሞስ፣ 2 ጢሞ. 4፡20
6. ኃጢአትና ሕመም ይያያዛሉ፣ በራቢዎችና በያዕቆብ (ዮሐንስ 9፡2፤ ያዕቆብ 5፡13-18)።
7. ፈውስ የአዲስ ኪዳን መተማመኛ (ዋስትና) አይደለም። እሱም የኃጢአት መዋጃ ክፍል አይደለም፣ ኢሳይያስ 53 እና መዝሙር 103 ላይ የተገለጸው።
8. እውነተኛ የሆነ ምሥጢር አለ፣ አንዳንዶች ለምን እንደተፈወሱ እና አንዳንዶች ለምን እንዳልተፈወሱ
9. ሊሆን የሚችለው፣ ምንም እንኳ ፈውስ በየዘመናቱ ቢኖርም፣ በኢየሱስ የሕይወት ዘመን ትርጉም ያለው ጭማሪ አሳይቷል፤ ይኸው መጨመር በድጋሚ ይከሰታል፣ ከመመለሱ ጥቂት ጊዜ በፊት።

◘ **"ፈወስከኝ"** ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

**30፡3 "ሲኦል. . .ጉድጓድ"** እነዚህ ሁለት ቃላት (ተመሳሳይ ትይዩ) የሚያመለክቱት መቃብርን ወይም የሙታን ማቆያ ስፍራን ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው? መዝ. 1፡6 ላይ።

በዚህ መዝሙር ላይ ፍጹም ተቃራኒ ትይዩ የተለመደ እንደሆነ ተገንዘብ። እሱም ያሳያል፣ እጅግ ርግጠኛ በሆነ የሕይወት መንገዶች፣ "ሁለቱ መንገዶች" የመዝሙር 1።

ለመልካም አጭር ማብራሪያ፣ ለ"ጉድጓድ" አይቪፒ፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ምናባዊነት (ምስል ከሳችነት)*፣ ገጽ 646-647 ተመልከት።

**30:4**
**ኢአመመቅ** **"መልካሞች"**
**አኪጀት** **"ቅዱሳን"**
**አየተመት** **"ታማኞች"**
**አእቅ** **"ታማኝ ሕዝቦች"**

ይህ ቅጽል (ቢዲቢ 339) የተመሠረተው ከስም ነው *ሄሰድ* (ቢዲቢ 338)፣ እሱም የኪዳን ታማኝነትን የሚገልጽ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 5:7 ላይ)።

1. በእግዚአብሔር በኩል፤ እሱ ታማኝ ነው ለኪዳን ተስፋዎቹ።
2. በታማኝ ተከታዮች በኩል፤ እሱ/እሷ ታዛዥና ቁርጠኛ መሆን አለባቸው፣ ለኪዳን ግዴታዎች።

እሱም የተለመደ መጠሪያ ነው፣ በመዝሙር ላይ፣ ለታማኝ የኪዳን ተከታዮች (ማለትም፣ መዝ. 4:3 እና ብዙ ሌሎችም)። በርካታ ትርጉሞች (አእት፣ አኢመቅ) 30:4-5 ተመልከት፣ እንደ ተለየ አንጓ፣ ታማኝ ተከታዮችን የሚጋብዝ፣ ያህዌን ለማመስገን እንዲገናኙ (የአንቀጽ ምድቦችን በዚህ መዝሙር በፊት ለፊት ገጽ ላይ ተመልከት)።

በዚህ ዐውድ ላይ እነሱ የሚጠሩት

1. ምስጋና ለመዘመር – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ *ፔል* ተተኳሪ
2. ምስጋና እንዲያቀርቡ – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል* ተተኳሪ

◘
**አአመመቅ፣ አየተመት፣**
**ጀፒኤስአኤ** **"ስም"**
**አኪጀት** **"መታሰቢያ"**
**አእቅ** **"ማሰብ"**
**አኢመቅ** **"የማይረሳ"**

ኤምቲ ስም አለው "መታሰቢያ" ወይም "ማስታወሻ" የሚል (ቢዲቢ 271፣ ሆሴ. 12:5)። እዚህ የሚያመለክተው የያህዌን የከበረ ባሕርይና ኃይለኛ ድርጊት ነው፣ በሕዝቡ አኳያ (cf. Ps. 6:5፤ 30:5፤ 97:12፤ 102:12፤ 111:4፤ 145:7)። የዕብራይስጡ ጽንሰ-ሐሳብ "ስም" እዚህ አለ፣ ቃሉ ሳይሆን። ሁለቱም በትይዩነት ተከስተዋል፣ መዝ. 135:13 እና ኢሳ. 26:8። ደግሞም "የመታሰቢያ ስም" የሚለውን ተተኳሪ ተገንዘብ፣ ዘጸ. 3:15 ላይ።

**30:5** ይህ ቁጥር የጸጋን አስደናቂነት ለወደቀው ስብዕና ይጠልፋል (*ያመጣል*) (ፍጹም ተቃራኒ ትይዩ)። ይህ የወደቀ ዓለም ነው፣ ነገር ግን ያህዌ የተሰበረው የኤድን ገነት ኅብረት ቋሚ እንዲሆን አልፈቀደም። የኃጢአትና ዓመጸኝነት መዘዝ አለ፣ ነገር ግን በጸጋው፣ በታማኝ ተከታይ እምነት ውስጥ በመማለድ (ኤፌ. 2:8-9)፤ ይቅርታና መታደስ አለ (መዝ. 103:8-14፤ኢሳ. 54:7-8)! ብቸኛው ቋሚ መዘዝ አለማመን ነው። እሱም የማይሰረይ ኃጢአት ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ ከታች)

የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ስንኞች የ30:5 ግሥ የላቸውም። የጊዜው አወቃቀር ሥነ-መለኮታዊ ነጥቡን አጽንዖት ይሰጣል

"ቍጣው ለጥቂት ጊዜ ነው፥
ሞገሱ ግን ለሕይወት ዘመን!"

ኤቢ (ገጽ 182) እንደሚለው "ለሕይወት ዘመን" (ቢዲቢ 213) ማለት "የዘላለም ሕይወት፣" ነው፣ መዝ. 21:4 ላይ በመመሥረት። ሆኖም፣ መዝ. 91:16 የተለመደው የዚህ ቃል የብኪ አጠቃቀም ነው፣ እሱም ይህን ሕይወት የሚያመለክት።

ስለ "ቍጣ" ተጨማሪ ሐሳብ ለመስጠት ያህል፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ። ብኪ ግንኙነት እንዳለ ተመልክቷል፣ በኃጢአት እና ሕመም መሐከል (ያዕቆብ 5:13-18)። ኢየሱስ ይህንን አመለካከት ያሻሻለው ይመስላል፣ ዮሐንስ 9:1-12። እግዚአብሔር ከኃጢአታችን አኳያ የሚፈርድብን ከሆነ ሁላችን እንታመማለን እንሞታለንም። አስደናቂው እውነት "ቁጣ" ይገባናል፣ ነገር ግን ምሕረት አግኝተናል፣ ጸጋ እና ፍቅር! ሆኖም፣ እኛ፣ ሁላችንም አልተፈወስንም (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ 30:2 ላይ)! እሱ ከእኛ ጋር ነው፣ በመከራችን (ሮሜ. 8:18-25፤ 2 ቆሮ. 4:17)።

◘ **"ቍጣው"** *ሥሩ* (ቢዲቢ 60) ከ "አፍንጫ" ጋር ይዛመዳል (ማለትም፣ ቀይ ፊት) ወይም "ሲቃ" (ያልተነገረ ነገር ግን የድምጽ ምልክት፣ ለሰው ስሜት)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አምላክ እንደ ሰው ሲገለጽ (ሥነ-ሰዋዊነት) መዝ. 2:4-6 ላይ

## ልዩ ርዕስ፡ ለሞት የሚያበቃ ኃጢአት ምንድነው?

*ሀ. ሥነ-ትርጓሜአዊ ታሳቢዎች*

1. ተገቢው መለያ መያያዝ የሚኖርበት ከ1 ዮሐንስ ታሪካዊ መቼት ጋር ነው

ሀ. የግኖስቲካዊ ሐሰተኛ መምህራን በቤተ ክርስቲያን መገኘት (1 ዮሐንስ 2:19,26፤ 3:7፤ 2 ዮሐንስ 7)

(1) "ሴሪንቲያን" የግኖስቲክ አስተሳሰብ፣ ማለትም ሰው ኢየሱስ የክርስቶስን መንፈስ ተቀበለ፣ በሚጠመቅበት ጊዜ፣ እናም የክርስቶሱ መንፈስ ከመስቀል ሞቱ በፊት ተወ (1 ዮሐንስ 5:6-8)

(2) "ዶሴቲክ" የግኖስቲክ አስተሳሰብ ማለትም ኢየሱስ መለኮታዊ መንፈስ ነው፣ እውነተኛ የሰው ልጅ ሳይሆን (1 ዮሐንስ 1:1-3)

(3) ግኖስቲሲዝም በሁለተኛው ክፍለ-ዘመን ጽሑፎች ላይ ተገልጧል፣ እሱም ሁለት የተለያዩ አተያዮችን ስለ ሰው አካል አንጸባርቋል

(ሀ) ደኅንነት ለአእምሮ የተገለጠ እውነት እስከሆነ ድረስ፣ የሰው አካል አስፈላጊነት የለውም፣ ለመንፈሳዊው ዓለም። ስለዚህ፣ የሚፈልገው ሁሉ ይኖረዋል። እነዚህ ዘወትር የሚጠቀሱት በጸጋ ከሕግ ነጻነት ወይም ነጻነታዊ ግኖስቲክስ ጋር ነው።

(ለ) ሌለኛው ቡድን የደመደመው ሥጋ የክፉ ውርስ እስከሆነ ድረስ (ማለትም፣ የግሪክ አስተሳሰብ)፣ ማንኛውም ሥጋዊ ፍላጎት መወገድ ይኖርበታል። እነዚህም ራስን የመካድ ግኖስቲክስ ተብለው ይጠራሉ።

ለ. እነዚህ የሐሰት መምህራን ቤተ-ክርስቲያንን ትተዋል (1 ዮሐንስ 2፡19)፣ ተጽዕኗቸው ግን አልተወም!

2. ተገቢው መለያ መያያዝ የሚኖርበት ከሙሉው መጽሐፍ ጽሑፋዊ ዐውድ ጋር ነው

ሀ. 1 ዮሐንስ የተጻፈው ሐሰተኛ ትምህርትን በመቃወም ነው፣ እናም የእውነተኛ አማኞችን ዋስትና ለማረጋገጥ

ለ. እነዚህ ሁለት ዓላማዎች ሊታዩ የሚችሉት በእውነተኛ አማኞች ፈተና ላይ ነው

(1) ዶክትሪናዊ

(ሀ) ኢየሱስ ፍጹም ሰው ነበር (1 ዮሐንስ 1፡1-3፤ 4፡14)

(ለ) ኢየሱስ ፍጹም ሰው ነው (1 ዮሐንስ 1፡2፤ 5፡20)

(ሐ) ሰዎች ኃጢአተኛ ናቸው፣ እናም ለቅዱሱ አምላክ ኃላፊነት አለባቸው (1 ዮሐንስ 1፡6,10)

(መ) ሰዎችም ይቅርታ አግኝተዋል፣ እናም በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ይሆናሉ፣

i. በኢየሱስ ሞት (1 ዮሐንስ 1፡7፤ 2፡1-2፤ 3፡16፤ 4፡9-10,14፤ 5፡6-8)

ii. በኢየሱስ ላይ ባለ እምነት (1 ዮሐንስ 1፡9፤ 3፡23፤ 4፡15፤ 5፡1,4-5,10-12,13)

(2) ተግባራዊ (አዎንታዊ)

(ሀ) የሕይወት ስልት ታዛዥነት (1 ዮሐንስ 2፡3-5፤ 3፡22,24፤ 5፡2-3)

(ለ) የሕይወት ስልት ፍቅር (1 ዮሐንስ 2፡10፤ 3፡11,14,18,23፤ 4፡7,11-12,16-18,21)

(ሐ) የሕይወት ስልት ክርስቶስን መምሰል (ኃጢአት አይሠራም፣ 1 ዮሐንስ 1፡7፤ 2፡6,29፤ 3፡6-9፤ 5፡18)

(መ) የሕይወት ስልት ድል በክፉ ላይ (1 ዮሐንስ 2፡13,14፤ 4፡4፤ 5፡4)

(ሠ) ቃሉ በእነርሱ ይኖራል (1 ዮሐንስ 1፡10፤ 2፡14)

(ረ) መንፈሱ አላቸው (1 ዮሐንስ 3፡24፤ 4፡4-6,13)

(ሰ) የተመለሰ ጸሎት (1 ዮሐንስ 5፡14-15)

(3) ተግባራዊ (አሉታዊ)

(ሀ) የሕይወት ስልት ኃጢአት (1 ዮሐንስ 3፡8-10)

(ለ) የሕይወት ስልት ጥላቻ (1 ዮሐንስ 2፡9,11፤ 3፡15፤ 4፡20)

(ሐ) የሕይወት ስልት ታዛዥነት (1 ዮሐንስ 2፡4፤ 3፡4)

(መ) ዓለምን መውደድ (1 ዮሐንስ 2፡15-16)

(ሠ) ክርስቶስን መካድ (አብ እና ወልድን የሚክድ 1 ዮሐንስ 2፡22-23፤ 4፡2-3፤ 5፡10-12)

3. ተገቢው መለያ የግድ መያያዝ የሚኖርበት በተወሰኑ ነገሮች ላይ ነው፣ በተገቢው ጽሑፍ ላይ (1 ዮሐንስ 5፡16-17)

ሀ. "ወንድም" የሚለው ቃል፣ የዮሐንስ 5፡16 የሚዛመደው ከእነዚያ ከሁለቱ የኃጢአት ድርጊቶች ጋር ነውን፣ ወደ ሞት ከማያመሩት እና ከእነዚያ የኃጢአት ድርጊቶች ወደ ሞት ከሚያመሩት?

ለ. ተላላፊዎቹ አንድ ጊዜ የቤተ-ክርስቲያን አባላት ነበሩን (1 ዮሐንስ 2፡19)?

ሐ. ጽሑፋዊ ጠቀሜታው ምንድነው የ፡

(1) ከ "ኃጢአት" ጋር አንቀጽ አለመኖሩ

(2) "ያያል" የሚለው ግሥ እንደ ሦስተኛ መደብ ሁኔታዊ የድርጊት የአሁን ሁኔታዊ ታሳቢ?

መ. የአንድ ክርስቲያን ጸሎት እንዴት (ያዕቆብ 5፡15-16) የዘላለምን ሕይወት ይመልሳል "*zōē*" የሌላውን ሰው፣ ኃጢአተኛው ራሱ ንስሐ ሳይገባ?

ሠ. 1 ዮሐንስ 5፡17 እንዴት ከኃጢአት ዓይነቶች ጋር ይዛመዳል (ለሞት የሚያበቃ፣ ለሞት የማያበቃ)?

ለ. ሥነ-መለኮታዊ ችግሮች

1. አንድ ተርጓሚ ይሄንን ጽሑፍ ማያያዝ ይኖርበታልን

ሀ. "ይቅር ከማይባል" ኃጢአት ጋር፣ ከወንጌል

ለ. "አንድ ጊዜ ከወጣ" ኃጢአት ጋር ከዕብራውያን 6 እና 10 ጋር

የዮሐንስ 1 ዐውደ-ጽሑፍ ትይዩ የሚመስለው ከፈሪሳውያን የማይሠረይ ኃጢአት ጋር ነው፣ በኢየሱስ ጊዜ (ማቴ. 12፡22-37፤ ማርቆስ 3፡2-29) ብሎም ከማያምኑ አይሁድ ጋር፣ ዕብራውያን 6 እና 10። ሦስቱም ወገኖች (ፈሪሳውያን፣ የማያምኑ አይሁድ፣ እና የግኖስቲክ የሐሰት መምህራን) ወንጌልን በግልጽ ሰምተዋል፣ ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስን ለማመን እምቢ ብለዋል።

2. ዘመናዊዎቹ ክፍለ-ሃይማኖታዊ ጥያቄዎች ሥነ-መለኮታዊ መለኪያ ሊሆኑ ይችላሉን፣ ይሄንን ጽሑፍ ለመመልከት?

ወንጌላዊነት የክርስቲያን ልምድ መጀመሪያን አጋንኖ ነበር እናም ቀጣይነት ያለውን የእውነተኛ እምነት የሕይወት

ስልት ማስረጃ ችላ ብሎት ነበር። የእኛ ዘመናዊዎቹ *ሥነ-መለኮታዊ* ጥያቄዎች የአንደኛውን ክፍለ-ዘመን ክርስቲያኖች ሊያስደነግጡ ይችሉ ነበር። እኛ "ርግጠኝነትን" እንሻለን፣ በተመረጡ የመጽሐፍ ቅዱሳዊ "የጽሑፍ ማጣራቶች" ላይ በመመሥረት እና በገዛ ራሳችን ሎጂካዊ አስተሳሰቦች ወይም ክፍለ-ሃይማኖታዊ ቅድመ-ግምቶች። የእኛ *ሥነ-መለኮታዊ* ጥያቄዎች፣ *መለያዎች*፣ እና ምልክቶች የሚያንጸባርቁት የራሳችንን አለመረጋጋት ነው። ተጨማሪ መረጃ እና ማብራሪያ እንሻለን፣ *መጽሐፍ* ቅዱስ ከሚሰጠው በላይ፣ ስለዚህ ስልታዊ *ሥነ-መለኮታችን* አንዳንድ አነስተኛ ጥቅሶችን ከቅዱስ ቃሉ ይወስድና ትልቅ ሎጂካዊ፣ ምዕራባዊ፣ የተወሰነ ዶክትሪንን ይሸምናል!

የኢየሱስ ቃላት ማቴዎስ 7 እና ማርቆስ 7 ላይ ያሉት ለጥንታዊቷ ቤተ-ክርስቲያን በቂ ነበሩ! ኢየሱስ ደቀ-መዛሙርት ይሻ ነበር፣ ውሳኔ ሳይሆን፣ የረጅም ጊዜ የሕይወት ስልት እምነት፣ የአጭር ጊዜ ስሜታዊ እምነት ሳይሆን (ማቴ. 13:10-23፤ ዮሐንስ 8:31-59)። ክርስትና የተለየ ያለፈ ድርጊት አይደለም፣ ነገር ግን ቀጣይነት ያለው ንስሐ፣ እምነት፣ *መታዘዝ*፣ እና ጽናት እንጂ። ክርስትና ወደ መንግሥተ ሰማያት መግቢያ ትኬት አይደለም፣ ባለፈው ጊዜ የተገዛ፣ አልያም የእሳት አደጋ ኢንሹራንስ ፖሊሲ አይደለም፣ አንዱን ከሕይወት ስልት ግለኝነት ለመጠበቅ፣ መልካምነት በሌለው ሕይወት!

3. ለሞት የሚያበቃ ኃጢአት የሚጠቅሰው *ሥጋዊ* ሞትን ነው ወይስ የዘላለም ሞትን? የዮሐንስ የ"*zōē*" አጠቃቀም፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የሚያመለክተው ተቃርኖው የሚያመለክተው የዘላለም ሞትን ነው። እግዚአብሔር ወደ ቤት ይወስዳል ማለት ይቻላልን (*ሥጋዊ ሞት*) ኃጢአት የሚሠሩትን ልጆች? የዚህ ዐውደ-ጽሑፍ አንድምታ (1) የባልንጀራ አማኞች ጸሎት እና (2) የተላላፊው ግላዊ ንስሐ አንድላይ ሆነው አማኞቹን እንደሚመልሱ ነው፣ ነገር ግን እነርሱ በአማኝ ማኅበረሱ ላይ መሳለቂያ የሚያመጣ የሕይወት ስልት መከተላቸውን ቢቀጥሉ፣ ውጤቱ "የመዳረሻ" ወይም ከዚህ ሕይወት ቅድመ-መነጠያ ሊሆን ይችላል (*ሐያሲያን በጠየቁ ጊዜ* በኖርማን ጌስለር እና ቶማስ ሆዊ፣ ገጽ 541)።

***መዝሙር : 30:6-9***

[6]**እኔም በደስታዬ።**
**ለዘላለም አልታወክም አልሁ።**
[7]**አቤቱ፥ በፈቃድህ ለሕይወቴ ኃይልን ሰጠሃት**
**ፊትህን መለስህ፥ እኔም ደነገጥሁ።**
[8]**አቤቱ፥ ወደ አንተ ጠራሁ፥**
**ወደ አምላኬም ለመንሁ።**
[9]***ወደ ጥፋት ብወርድ በደሜ ምን ጥቅም አለ?***
***አፈር ያመሰግንሃልን? እውነትህንም ይናገራልን?***

**30:6-9** ይህ አንጓ የሚያንጸባርቀው የኪዳን ተስፋዎችን *መፈጸም* ነው፣ የሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 28። ያህዌ ሕዝቦቹን ለማበልጸግ ይሻል፣ ለዓለም ባሕርዩን ለማሳየት። መዝሙረኛው፣ እንደ ታማኝ ተከታይ፣ ያህዌ ያደረገለትን ያስረግጣል።

1. አበለጸገው
2. *መረጋጋትን* ሰጠው (ማለትም፣ "ፈጽሞ አልናወጥም")
3. ብርቱ አደረገው (ማለትም፣ በተራራ ዘይቤ፤ LXX "የእኔ ክብር" የሚል አለው)
4. ጸሎቱን ሰማ
5. ከሞት አዳነው፣ ስለዚህ የያህዌን ታማኝነት ያመሰግናል (ቢዲቢ 54)

ኤቢ (ገጽ 182) ይሄንን አንጓ የሚመለከተው እንደ ማስጠንቀቂያ ነው፣ በትዕቢት ኃጢአት ላይ። *የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ* (ገጽ 282) እሱን የሚመለከተው እንዳለፈ ተገቢ ያልሆነ ልምምድ ነው። ሆኖም፣ እኔ የሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 28ን መመካትን ነው። *ማስታወሻ መጽሐፉ* የሚያስረግጠው ይህ መዝሙር፣ እንደ መዝሙር 29 ተገላቢጦሻዊ ፈርጅ ነው። ይህ እውነት ከሆነ፣ እንግዲያውስ የመስቀልያው መካከል ዋነኛው እውነት መሆን አለበት። ነገር ግን መካከለኛው፣ ቁጥር 6 መሆኑን ተገንዘቡ፣ ይኸውም፣ ሁለቱም ዩቢኤስ *ማስታወሻ መጽሐፍ* እና ኤቢ የሚሉት ተገቢ ያልሆነ ልምምድ ነው። ሁለቱን መንገዶች ልትሰጡት አትችሉም!

**30:7ለ** ቁ. 7ለ ከቁ. 7ሀ፣ሐ ጋር እንደሚገጥም ርግጠኝነት የለም። ሁለቱ ግሦች (የተጠናቀቁ) የተመቻቸ ሁኔታን ይገልጻሉ።

1. ፊትህን መለስክ – ቢዲቢ 711፣ ኬቢ 771፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ፣ "ፊት፣" የሚያመለክተው አካላዊ መገኘትን ነው፣ እሱ ያህዌ እንደ ተወው ተሰምቶታል፣ አልተገኘም፣ ጸሎቱን አይሰማም።
2. እኔ (ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) በፍርሃት ተመትቻለሁ – ቢዲቢ 96፣ ኬቢ 111፣ *ኒፋል* ቦዝ አንቀጽ። ይህ ቃል ፍችው "መታወክ፣" "መፍራት፣" ወይም "መሸበር፣" ነው ኢዮብ 4:5፤ 23:15፤ መዝ. 6:4፤ 83:18፤ 90:7፤ 104:29፤ መዝ. 13:8፤ 21:3፤ ኤር. 51:32፤ ሕዝ. 26:18።

ጄፒኤስኦኤ ይሄንን ቁ. 7ለ የሚመለከተው ከቁ. 8 ጋር በተቃርኖ ነው፣ ያህዌ መዝሙረኛውን አድርጎታል "ጽኑ እንደ ታላቅ ተራራ፣" ግን ፊቱን ሲሰውር/የሰወረ እንደሁ "ሽብር" *ያመጣል*። ስለዚህ፣ ወደ ያህዌ በጸሎት ተጣራ (ቁ. 8)። ብልጽግና ብቻውን፣ የኪዳን ብልጽግና እንኳ ቢሆን (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 28) በቂ አይሆንም! እግዚአብሔር ያስፈልገናል! የእርሱ መገኘትና ደስታ

ሊሰማን ይገባል! የተፈጠርነው (ዘፍ. 1፡26-27፤ 3፡8) ከእግዚአብሔር ጋር ለሚሆን ኅብረት ነው። ምንም፣ ሌላ ምንም ከዚህ መሻት ጋር ሊገጥም አይችልም!

**30፡9** ሁለት ሪቶሪካዊ (አንደበተ-ርቱዕነት) ጥያቄዎች አሉ፣ ከዐውደ-ጽሑፉ፣ "ምንም" ምላሽ የሌላቸው።

▣ ***"አፈር"*** ይህ (ቢዲቢ 779) ዘይቤአዊ ገለጻ ነው፣ ለሞት (መዝሙር 22:15፣19፤ ኢሳይያስ 26:19፤ 29:4) ወይም ሲኦል/ጉድጓድ። ሰዎች የተሠሩት ከሸክላ/አፈር ነው (ዘፍ. 2፡7) እናም ወደ አፈር በሞት እንመለሳለን (ዘፍ. 3፡19)።

▣ ***"አፈር ያመሰግንሃልን?"*** በብኪ ሞት ንቁ ነበር፣ ግን ጸጥ ያለ፣ ሕላዌ (መዝ. 6:5፤ 88:11-12፤ 115:7፤ መክ. 9:10፤ ኢሳ. 38:18-19)።

▣ ***"ታማኝነትህንም"*** ይህ "አሜን" ነው (ቢዲቢ 54)፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝሙር 12፡1 ላይ።

ያህዌ የታመነ ነው (ቢዲቢ 54) ታማኝም ነው (ቢዲቢ 338) ለኪዳኑ። እሱ ብቻውን የማይለወጥ ነው (ሚል. 3:6፤ መዝ. 102:27፤ ያዕቆብ 1:17፤ ደግሞም ዕብ. 13:8 ተመልከት)። የእኛ ተስፋ፣ እንደ ታማኝ ተከታዮች፣ በማይለወጠው፣ መሐሪው በያህዌ ባሕርይ ላይ ነው።

***መዝሙር ፡ 30፡10-12***

**10 እግዚአብሔር ሰማ ማረኝም**
**እግዚአብሔር ረዳቴ ሆነኝ።**
**11 ክብሬ ትዘምርልህ ዘንድ ዝምም እንዳትል ልቅሶዬን ለደስታ ለወጥህልኝ፥**
**ማቄን ቀድደህ ደስታንም አስታጠቅኸኝ።**
**12 አቤቱ አምላኬ፥ ለዘላለም አመሰግንሃለሁ።**

**30፡10-12** ይህ አንጓ በሦስት የጸሎት ጥያቄዎች ይጀምራል (ተተኳሪዎች)።

1. ስማ – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. ማረኝም – ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. ረዳቴ ሆነኝም (ቢዲቢ 740፣ ኬቢ 810) – ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ *ቃል ተተኳሪ*

የያህዌ ምላሽ በመዝሙረኛው ላይ ያሳደረውን ተመልከት።

1. ልቅሶዬን ለደስታ ለወጥክልኝ
2. ማቄን ቀደድህ ደስታንም አስታጠቅኸኝ ("ደስታ" ቅኔአዊ መንገድ ነው፣ ማቅን የሚቃረን፣ ማለትም፣ የክብረ-በዓል ልብስ)
3. የምስጋና ዝማሬ እንዲያቀርብ አደረገው፣ ዝምም አይልም
4. ለዘላለም እንዲያመሰግን አደረገው

**30፡11 *"ማቅ"*** ይህ የሚለበሰው ለኀዘን ምልክት ነው።

## ልዩ ርዕስ፡ የኀዘን *ሥነ-ሥርዓት*

እስራኤላውያን ለተወዳጅ ሙቶቻቸው እና ለግላዊ ንስሐ፣ ብሎም ሊጋራ በደሎች ኀዘንን የሚገልጹት በበርካታ መንገዶች ነው፡

1. ልብስን መቅደድ፣ ዘፍ. 37:29፣34፤ 44:13፤ መሳ. 11:35፤ II ሳሙ. 1:11፤ 3:31፤ I ነገሥ. 21:27፤ ኢዮብ 1:20
2. ማቅ መልበስ፣ ዘፍ. 37:34፤ II ሳሙ. 3:31፤ I ነገሥ. 21:27፤ ኤር. 48:37
3. ጫማን ማውለቅ፣ 2ኛ ሳሙ. 15:30፤ ኢሳ. 20:3
4. እጅን ራስ ላይ ማድረግ፣ 2ኛ ሳሙ. 13:19፤ ኤር. 2:37
5. በራስ ላይ አቧራ መነስነስ፣ ኢያ. 7:6፤ I ሳሙ. 4:12፤ ነህ. 9:1
6. መሬት ላይ መቀመጥ፣ ሰቆ. 2:10፤ ሕዝ. 26:16 (መሬት ላይ መጋደም፣ II ሳሙ. 12:16)፤ ኢሳ. 47:1
7. ደረትን መድቃት፣ I ሳሙ. 25:1፤ II ሳሙ. 11:26፤ ናሆ. 2:7 (የ"ኀዘን" ሥርወ-ፍቺ፣ " ቢዲቢ 704)
8. ገላን መቁረጥ፣ ዘዳ. 14:1፤ ኤር. 16:6፤ 48:37
9. ጾም፣ II ሳሙ. 1:12፤ 12:21-23፤ I ነገሥ. 21:27፤ I ዜና. 10:12፤ ነህ. 1:4
10. የኀዘን እንጉርጉሮ፣ II ሳሙ. 1:17፤ 3:31፤ II ዜና. 35:25
11. ፀጉርን መላጨት (ፀጉርን መንጨት ወይም መላጨት)፣ ኤር. 48:37
12. ፂምን ባጭሩ መቁረጥ፣ ኤር. 48:37
13. ራስን ወይም ፊትን መሸፈን፣ II ሳሙ. 15:30፤ 19:4

**30፥12 "ነፍሴ ትዘምርልህ ዘንድ"** "ነፍሴ" በጥሬው "ክብሬ" ነው (ቢዲቢ 458)። ተመሳሳዮቹ ተናባቢዎች ደግሞ የሚሉት "ጉበት" ነው። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 209) የሚለው፣ እሱን መረዳት የሚቻለው እንደ

1. ዘማሪውን ራሱን ለመጥቀስ (ማለትም፣ የውስጥ ማንነቱን — ጉበት) በቃሉ (LXX፣ አኪጀት፣ አየተመት፣ አእቅ፣ ጂፒኤስኦኤ)
2. መከሰቻው፣ "ክብሬ፣" ያህዌን ያመለክታል

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. እግዚአብሔር ሁሉንም ታማኝ ተከታዮች ይፈውሳልን?
2. ቁጥር 5 ለምን እጅግ ጠቃሚ እንደሆነ አስረዳ።
3. ቁጥር 6 አዎንታዊ መግለጫ ነው ወይስ አሉታዊ?
4. ቁጥር 9 እና 12 እንዴት ይዛመዳሉ?

## መዝሙር 31
## የአዲሶቹ ትርጕሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የአቤቱታ እና የምስጋና መዝሙር<br>ኤምቲ መግቢያ<br>"ለመዘምራን አለቃ።" የዳዊት መዝሙር። | ጌታ፣ በመከራ ጊዜ መጠጊያ | ከግል ጠላቶች የመታደግ ጸሎት | በእግዚአብሔር የመታመን ጸሎት | ጸሎት በመከራ ጊዜ |
| 31:1-5 | 31:1-2 | 31:1-2 | 31:1-2 | 31:1-2ሀ |
| | | | | 31:2ለ-3 |
| | 31:3-5 | 31:3-5 | 31:3-5 | |
| | | | | 31:4-5ለ |
| | | | | 31:5ሐ-7ሀ |
| 31:6-8 | 31:6-8 | 31:6-8 | 31:6-8 | |
| | | | | 31:7ለ-8 |
| 31:9-13 | 31:9-13 | 31:9-10 | 31:9-10 | 31:9 |
| | | | | 31:10 |
| | | 31:11-13 | 31:11-13 | 31:11 |
| | | | | 31:11ሐ-12 |
| | | | | 31:13 |
| 31:14-18 | 31:14-18 | 31:14-18 | 31:14-18 | 31:14-16 |
| | | | | 31:17-18 |
| 31:19-22 | 31:19-20 | 31:19-20 | 31:19-20 | 31:19 |
| | | | | 31:20 |
| | 31:21-22 | 31:21-22 | 31:21-22 | 31:21-22 |
| 31:23-24 | 31:23-24 | 31:23-24 | 31:23-24 | 31:23-24 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. እጅግ በርካታ መዝሙሮች አሉ፣ ደራሲው ከእግዚአብሔር ርዳታ የሚሻበት፣ በጠላቶቹ ላይ። አንዱ ሊደነቅ ይችላል

1. እነዚህ ጠላቶች እነማን እንደሆኑ?
2. መዝሙረኛው ስለምን ዘወትር እንደተነጠለ ይሰማዋል?
3. እነዚህ አብዛኞቹ የተጻፉት በተመሳሳይ ጊዜ ነውን፣ በመዝሙረኛው ሕይወት (ዳዊት ሊሆን ይችላል)?

ለ. መዝሙረኛው በርካታ ጉዳዮች ገጥመውታል።
1. የግል ኃጢአት እና የእሱም አእምሯዊና አካላዊ መዘዝ (ዝከ. 31፡1-12)
2. ግለሰባዊ ጥቃቶች
   ሀ. በጠላቶቹ
   ለ. ባልንጀሮቹ
   ሐ. ወዳጆቹ

ሐ. የጠላቶች ድርጊቶች ባሕርይ ያደረጉት
1. እሱን በመረብ ለማጥመድ፣ ቁ. 4
2. እሱ ወደ ጣዖታት እንዲመለከት ማድረግ፣ ቁ. 6
3. ስሙን ማጥፋት፣ ቁ. 11፣13፣20
4. በእርሱ ላይ በክፉ መምከር፣ ቁ. 13፣20
5. እሱን ማሳደድ፣ ቁ. 15
6. ሐሰተኛ አንደበት አላቸው፣ ቁ. 18
7. በትዕቢት መናገር፣ ቁ. 18

መ. ብዙዎቹ/አብዛኞቹ መዝሙራት በመጽሐፍ አንድ ተመሳሳይ ጭብጥ እና ቃላት አላቸው። ይህም ሊያንጸባርቅ የሚችለው ያልታወቀ አዘጋጅነት (ኤዲቲንግ) ወይም የማጠናቀር አጀንዳ ነው። የሆን ተብሎ አወቃቀር አለ፣ የመዝሙርን የተለያዩ መጻሕፍት (የመዝሙርን መግቢያ ተመልከት) ነገር ግን ዘመናዊዎች ምን እንደነበረ ርግጠኛ አይደሉም።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 31፡1-5**

**ለመዘምራን አለቃ በማድነቅ ጊዜ የዳዊት መዝሙር።**
**1አቤቱ አንተን ታመንሁ**
**ለዘላለም አልፈር**
**በጽድቅህም አድነኝ።**
**2ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል፥ ፈጥነህም አድነኝ**
**ታድነኝ ዘንድ መታመኛ አምላክና**
**የመጠጊያ ቤት ሁነኝ።**
**3አምባዬና መጠጊያዬ አንተ ነህና**
**ስለ ስምህ መንገዴን አቅና ምራኝም።**
**4አንተ መታመኛዬ ነህና**
**ከደበቁብኝ ወጥመድ አውጣኝ።**
**5በእጅህ ነፍሴን እሰጣለሁ**
**የእውነት አምላክ አቤቱ፥ ተቤዠተኸኛል።**

**31፡1-5** እጅግ ግለሰባዊ በሆነ መንገድ ደራሲው ወደ ያህዌ እንደሚቀርብ ተገንዘብ። የተውላጠ ስሞችን ቁጥር ተገንዘብ። መጽሐፍ ቅዱሳዊው እምነት ግላዊ መታመን ነው፣ በአካላዊው አምላክ። እሱ በመነሻው ስለ ሕግ ወይም ይልቁንም የሞራል ደንብ አይደለም ነገር ግን ስለ ግላዊ ያልተጠበቀ ግንኙነት ነው! ያልተጠበቀው ግንኙነት ሁሉንም ነገር ይቀይረዋል! ሌላው ሁሉ በእርሱ ላይ ይመሠረታል።

▣ ይህ አንጓ በርካታ የጸሎት ጥያቄዎችን ይዟል።
1. ፈጽሞ አልፈር – ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ *ቃል ኅብራዊ*፤ ይህ ኀፍረት ሊያያዝ የሚችለው ከዳዊት ኃጢአት ጋር ነው (መዝሙር 32፤ 51) ወይም ሌሎች የእርሱን መልካም ስም ወይም ሐሳብ ሲያጠቁ ነው፣ መዝ. 25:2-3፣20፤ 31:1፣17፤ 35:26፤ 69:6፤ 119:6፣46፣78፣80። ኀፍረት አንዳንዴ በያህዌ መተው ይሆናል (ዝከ. ኒዶቲ፣ ቅጽ. 1፣ ገጽ. 621-627)።
2. አድነኝ – ቢዲቢ 812፣ ኬቢ 930፣ *ፔል ተተኳሪ*
3. ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል – ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 17:6፤ 71:2፤ 86:1፤ 88:2፤ 102:2
4. ታደገኝ – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
5. ዐምባዬ – ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ *ቃል ተተኳሪ*

6. ምራኝ – ቢዲቢ 634፣ ኬቢ 685፣ *ቃል ተተኳሪ*
7. ምራኝ – ቢዲቢ 624፣ ኬቢ 675፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
8. ከወጥመዳቸው አውጣኝ – ቢዲቢ 422፣ ኬቢ 425፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*

የእርሱ የጸሎት ጥያቄ የተመሠረተው

1. ራሱን ለያህዌ በመስጠቱ፣ ቁ. 5
2. ያህዌ ዋጅቶታል፣ ቁ. 5 (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 19፡14 ላይ)
3. ያህዌ ብርታቱ ነው፣ ቁ. 4
4. ያህዌ የእውነት/የታማኝነት አምላክ ነው፣ ቁ. 5 (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 12፡1 ላይ)

**31፡1 "መታመኛ"** ይህ የሚጠቅሰው ጠንካራ የመሸሸጊያ ስፍራ ነው፣ ለደኅንነትና ለጥበቃ። መዝ. 2፡12 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት።

▣ **"ጽድቅ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 1፡5 ላይ።

**31፡2 "ዓለት"** መዝ. 18፡2 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት። ሁለት የተለያዩ የዕብራይስጥ ቃላት አሉ "ዓለትን" የሚተረጉሙ፤ ቁ. 2 — ቢዲቢ 700 ላይ፤ ቁ. 3 — ቢዲቢ 849 ላይ። ሁለቱም የሚያመለክቱት የመረጋጋት፣ የጥበቃ፣ እና የደኅንነት ስፍራን ነው (ዘዳ. 32፡4፣15፣18፣30)።

**31፡3 "ምሽግ"** ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 18፡2 ላይ።

▣ **"ስለ ስምህ"** መዝሙር 23፡3 እና 25፡11 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት። እሱም ያየህዌን ባሕርይ ይወክላል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት፣ መዝ. 9፡10ለ ላይ።

**31፡3-4** ተለጣጣቂ የሆኑትን ያልተጠናቀቁዎች ተመልከት፣ ቀጣይነት ያላቸውን፣ በሂደት ላይ የሆኑትን ድርጊቶች የሚገልጹትን።

1. መምራት – ቢዲቢ 634፣ ኬቢ 685፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*
2. መምራት – ቢዲቢ 624፣ ኬቢ 675፣ *ፔል ያልተጠናቀቀ*
3. ማውጣት – ቢዲቢ 422፣ ኬቢ 425፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*

**31፡4 "መረብ"** ይህ የአደን መሣርያ ነው (ቢዲቢ 440)። እሱም በዘይቤነት ሰዎችን ለማደን ወይም ለመጥለፍ ጥቅም ላይ ውሏል (መዝ. 9:15፤ 10:9፤ 35:7-8፤ 57:6፤ 140:5)።

**31:5 "በእጅህ ነፍሴን እሰጣለሁ"** ይህ በኢየሱስ ተጠቅሷል፣ በመስቀል ላይ፣ ከመሞቱ ጥቂት ቀደም ብሎ በፊት (ሉቃስ 23:46)።

ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ 823፣ ኬቢ 955፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*) ሰፊ የፍች መስክ አለው። እዚህ የሚጠቅሰው ቀጣይነት ያለውን እምነት ነው። ይህም እምነት መሠረት የሚያደርገው በእግዚአብሔር ማንነት ላይ ነው (ማለትም፣ "የእውነት አምላክ፣" "ታማኝ አምላክ") የመዝሙረኛው *ሥራ* ሳይሆን።

▣ **"እጅ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝሙር 7፡3-4 ላይ።

▣ ***"መንፈስ"*** ይህ የዕብራይስጥ ቃል *ሩህ* ነው (ቢዲቢ 924)። እዚህ እሱ የማይታየው የሕይወት ኃይል ነው፣ ከያህዌ የሕይወት እስትንፋስ ጋር የተያያዘ፣ አዳም ላይ፣ ዘፍ. 2፡7። እሱም *ሥጋን* ሲተው፣ *ያ ሥጋ* ወደ ሙታን ማቆያ ስፍራ ይሄዳል (ሲኦል፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡6 ላይ) ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

### ልዩ ርዕስ፡ እስትንፋስ፣ ነፋስ፣ መንፈስ ( רוּחַ እና *pneuma*)

የዕብራይስጡ ቃል *ሩህ/ruach* (ቢዲቢ 924) እና የግሪኩ ቃል *ኒዩማ/pneuma* (ዮሐንስ 3፡5፣8) ሊል የሚችለው "መንፈስ፣" "እስትንፋስ" ወይም "ነፋስ" ነው (ዮሐንስ 3፡5፣8)። መንፈስ ዘወትር ለፍጥረት ጋር ይያያዛል (ዘፍ. 1:2፤ Job 26:13፤ መዝ. 104:29-30፤ 147:14-18)። ብኪ በግልጽ አይገልጽም በእግዚአብሔርና በመንፈስ መካከል ያለውን ግንኙነት። ኢዮብ 28:26-28፤ መዝ. 104:24 እና ምሳ. 3:19፤ 8:22-23, ላይ እግዚአብሔር ጥበብን ተጠቅሟል (እንስታይ ስም) ሁሉንም ነገር ለመፍጠር። በአኪ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ወኪል ተብሏል፣ በፍጥረት ላይ (ዮሐንስ 1:1-3፤ 1 ቆሮ. 8:6፤ ቆላ. 1:15-17፤ ዕብ. 1:2-3)። በመዋጀት ላይ እንደሆነው ሁሉ፣ እንዲሁ በፍጥረት ላይ፣ ሦስቱም የአምላክ አካላት በሞላ ተሳትፈዋል። ዘፍጥረት 1 ራሱ ለሁለተኛ ምክንያት ምንም አጽንዖት አይሰጥም።

***መዝሙር ፡ 31፡6-8***

[6]**ከንቱ ምናምንቴነትን የጠበቁትን ጠላህ**

**እኔ ግን በእግዚአብሔር ታመንሁ።**
**[7]መከራዬን አይተሃልና፥**
**ነፍሴንም ከጭንቀት አድነሃታልና**
**በምሕረትህ ደስ ይለኛል ሐሤትም አደርጋለሁ።**
**[8]በጠላቴ እጅ አልዘጋኸኝም፥**
**በሰፊም ስፍራ እግሮቼን አቆምህ።**

**31፡6-8** ይህ አንጓ በተጠናቀቁ ተሞልቷል፣ ይኸውም የተጠናቀቀ ወይም የተረጋጋ ሁኔታን የሚያመለክት።

1. ከንቱ ጣዖታትን የሚከተሉትን ጠላሁ – ቢዲቢ 971፣ ኬቢ 1338፣ *ቃል* የተጠናቀቀ። የመዝሙረኛው ጥያቄዎች ጥብቀት፣ ያህዌ እንዲፈርድለት፣ በርዕዮተ-ዓለሙ ላይ የተመሠረተ ነው (ማለትም፣ ዓለምን እንደ እግዚአብሔር ወኪል መመልከት)። እሱ የያህዌን ኪዳን የሚያፈርሱትን ወይም ችላ የሚሉትን ጠልቷል። LXX "ጠላህ" የሚል አለው።
2. በያህዌ ታመንሁ – ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፤ ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ መዝ. 4:5፤ 13:5፤ 25:2፤ 26:1፤ 28:7፤ 31:6፣14፤ 52:8፤ 56:3፣4፣11፤ 91:2። "እግዚአብሔርን መፍራት የጥበብ መጀመሪያ ከሆነ" (ምሳ. 1:7)፣ እንግዲያውስ ማመን እሱን በግል ለማወቅ ቁልፍ ነው።
3. ያህዌ መከራውን ተመልክቶለታል – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ *ቃል* የተጠናቀቀ (ዘጸ. 3:7-8)
4. ያህዌ ችግሩን አውቆለታል – ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ *ቃል* የተጠናቀቀ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 1:6)
5. ያህዌ በጠላቶቹ እጅ አሳልፎ አልሰጠውም – ቢዲቢ 688፣ ኬቢ 742፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ
6. ያህዌ በሰፊ ስፍራ እግሮቹን አቁሟል – ቢዲቢ 763፣ ኬቢ 840፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 18:19፤ 118:5፤ ሰፊ ስፍራ የጠባብ ስፍራ/ሰርጥ ተቃራኒ ነው፣ እሱም የመከራ ዘይቤ የሆነ (መዝ. 4:1፤ 18:19፤ 118:5)

**31፡7** ይህ ቁጥር ሁለት *ቃል* ኅብሮች አሉት።

1. እደሰታለሁ – ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189
2. ደስ ይለኛል – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ቸርነት"** |
| **አኪጀት፣ LXX** | **"ምሕረት"** |
| **አየተመት** | **"ጽኑ ፍቅር"** |
| **አእቅ** | **"ቋሚ ፍቅር"** |
| **አኢመቅ** | **"የታመነ ፍቅር"** |
| **ጄፒኤስአኤ** | **"ታማኝነት"** |
| **የተእመቅ** | **"የማይወድቅ ፍቅር"** |

እነዚህ ሁሉ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች መግለጽ የሚሞክሩት ኃይለኛውን የኪዳን ስም *ሄሰድ* ነው። እሱም የያህዌን የማይሰበር የኪዳን ቁርጠኝነት ይገልጻል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 5:7 ላይ።

**መዝሙር ፡ 31፡9-13**

**[9]ተቸግሬአለሁና አቤቱ ምራኝ**
**ዓይኔም ከኃዘን የተነሣ ተፈጀች፥ ነፍሴም ሆዴም።**
**[10]ሕይወቴ በኀዘን አልቃለችና፥**
**ዓመታቴም በልቅሶ ጨኸት**
**ኃይሌ በችግር ደከመ፥**
**አጥንቶቼም ተነዋወጡ።**
**[11]በጠላቶቼ ዘንድ ተነወርኹ፥**
**ይልቁንም በጎረቤቶቼ ዘንድ፥**
**ለሚያውቁኝም ፍርሃት ሆንሁ**
**በሜዳ ያዩኝም ከእኔ ሸሹ።**
**[12]እንደ ሞተ ሰው ከልብ ተረሳሁ፥ እንደ ተበላሸ ዕቃም ሆንሁ።**
**[13]የብዙ ሰዎችን ስድብ ሰምቻለሁና**
**በዙሪያው ፍርሃት ነበረ**
**በላዩ በአንድነት በተሰበሰቡ ጊዜ**
**ነፍሴን ለመንጠቅ ተማከሩ።**

**31፡9-13** ይህ አንጓ ከፊሉን የሰው አካል ተጠቅሟል የመዝሙረኛውን ችግር ለመግለጽ (ቢ.ዲ.ቢ. 865 II)።

1. ዓይን (ቢ.ዲ.ቢ. 744)፣ ቁ. 9፣ መዝ. 6:7፤ 38:10
2. ነፍስ (ቢ.ዲ.ቢ. 659)፣ ቁ. 10 (ማለትም፣ ነፍሽ፣ ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 3:2 ላይ)
3. አካል (ቢ.ዲ.ቢ. 105)፣ ቁ. 10
4. አካል ("አጥንቶቼ፣" ቢ.ዲ.ቢ. 782)፣ ቁ. 10

ጭንቀት (እንደ ኃጢአት፣ ቁ. 10ሐ፤ መዝሙር 32፣ 51) ሥጋዊ መገለጫዎችን ይፈጥራል።

1. ኀዘን
2. ሳግ
3. አቅም ማጣት
4. አጥንቶች ይነዋወጣሉ (ግሥ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 799፣ ኬቢ. 898፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ሁለቴ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ቁ. 9 እና 10 ላይ እንዲሁም ሌላ አንድ ጊዜ በብኪ፣ መዝ. 6:7)

ብዙ ብዙ ዘመናዊ ሕክምና በአእምሮና በአካል መካከል ያለውን ግንኙነት መገንዘብ ነው። እነርሱ አንድ ናቸው (ዝኪ. ቁ. 12)።

**31፡11** ይህ የስድብ ቃልና መረበሽ፣ ይህን የመሰለ አካላዊ ተጽዕኖ ያለው፣ ማኅበራዊ ተጽዕኖም ያመጣል።

1. መዘበቻ ሆኛለሁ፣ በተለይም ለጎረቤቶቼ።
2. ለሚያውቁኝም ፍርሃት ሆኛለሁ።
3. ሰዎችም ከእኔ ሸሹ
4. ተረሳሁ (ከሐሳብ ውጭ ሆንኩ) እንደ ሞተ ሰው

**31፡13** ይህ ቁጥር የሚገልጸው የጠላቶቹን ድርጊት ነው።

1. ሰድበውታል (ማለትም፣ የሐሰት ቃላቸው በሚቀጥለው ስንኝ ላይ ናቸው፣ "በየቦታው ሽብር")
2. በእርሱ ላይ በሐሰት ተማክረዋል
3. አሲረዋል (ቢ.ዲ.ቢ. 273፣ መዝ. 37:12) ነፍሱን ለመውሰድ (ትይዩ ከቁ. 2 ጋር)

ከእነዚህ ድርጊቶች አኳያ፣ ተተኳሪው "ጌታ ሆይ፣ ቸርነትህን አብዛልኝ" የቁጥር 9 መረዳት የሚቻል ነው!

**መዝሙር ፡ 31፡14-18**

**[14]አቤቱ፥ እኔ ግን በአንተ ታመንሁ**
**አንተ አምላኬ ነህ አልሁ።**
**[15]ርስቴ በእጅህ ነው**
**ከጠላቶቼ እጅና ከሚያሳድዱኝ አድነኝ።**
**[16]ፊትህን በባሪያህ ላይ አብራ፥**
**ስለ ምሕረትህም አድነኝ።**
**[17]አቤቱ፥ አንተን ጠርቻለሁና አልፈር**
**ክፉዎች ይፈሩ በሲኦልም ዝም ይበሉ።**
**[18]በድፍረትና በትዕቢት**
**በመናቅም በጻድቅ ላይ የሚናገሩ**
**የሽንገላ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ።**

**31፡14-18** ይህ አንጓ በርካታ አጽንዖታዊ የጸሎት ጥያቄዎች አሉት፣ የሚመሠረተውም

1. የመዝሙረኛው እምነት፣ በያህዌ ላይ (ቃል የተጠናቀቀ፣ ዝኪ. ቁ. 6)፣ ቁ. 14
2. ያህዌ አምላኩ ነው፣ ቁ. 14
3. ሕይወቱ በያህዌ እጅ ላይ ነው፣ ቁ. 15

ጥያቄዎቹ እነሆ።

1. አድነኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 664፣ ኬቢ. 717፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ መዝ. 7:2፤ 18:17፤ 22:20፤ 31:2፤ 39:8፤ 51:14፤ 59:1፤ 69:14፤ 109:21፤ 119:170፤ 120:2፤ 142:6፤ 143:9፤ 144:7፣11፤ ይህ የታማኝ ተከታዮች ልብ ጩኸት ነው፣ መዳን ከመንፈሳዊ፣ አእምሯዊ፣ እና አካላዊ የሕይወት ገጽታዎች፣ በወደቀው ዓለም
2. ፊትህን በእኔ ላይ አብራ – ቢ.ዲ.ቢ. 21፣ ኬቢ. 24፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ ዘኍ. 6:25-26፤ መዝ. 4:6፤ 67:1፤ 80:3፣7፣19፤ 119:135
3. ስለ ምሕረትህም አድነኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 446፣ ኬቢ. 448፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ በርካታ ጊዜ መዝሙራት ላይ
4. አልፈር – ቢ.ዲ.ቢ. 101፣ ኬቢ. 116፣ ቃል ኀብራዊ
5. ክፉዎች ይፈሩ – ቢ.ዲ.ቢ. 101፣ ኬቢ. 116፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
6. በሲኦል ዝም ይበሉ – ቢ.ዲ.ቢ. 198፣ ኬቢ. 226፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
7. ሐሰተኛ ከንፈሮች ድዳ ይሁኑ – ቢ.ዲ.ቢ. 47፣ ኬቢ. 57፣ ሂፉል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

**31:15 *"ቀኖቼ በእጅህ ናቸውና"*** *ታማኝ ተከታዮች ያምናሉ፣ ጊዜና ዘላለማዊነት በእግዚአብሔር ቅድመ-እውቅናና ቁጥጥር ሥር መሆናቸውን።* (ኢዮብ 14:5፣16፤ 28:24፤ 31:4፤ 34:21፤ መዝ. 139:1-16፣ በተለይ ቁ. 16)።

**31:17** *ተቃርኖውን ተገንዘብ።*

1. *መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር ይናገራል*

2-3. ክፉው ዝም ብሏል (ማለትም፣ ሙት) ወይም ደግሞ እነርሱ በትዕቢት፣ በኩራት እና በንቀት ይናገራሉ

ሰዎችን በሚናገሩት ታውቋቸዋላችሁ (ማቴ. 12:35-37)። ምላስ ልብን ይገልጣል!

***መዝሙር ፡ 31:19-22***

[19]***በአንተ ለሚያምኑ በሰው ልጆች ፊት ያዘጋጀሃት***
***ለሚፈሩህም የሰወርሃት፥***
***ቸርነትህ እንደ ምን በዛች!***
[20]***በፊትህ መጋረጃ ከሰው ክርክር ትጋርዳቸዋለህ፥***
***በድንኳንህም ከአንደበት ክርክር ትሸፍናቸዋለህ።***
[21]***በተከበበ ከተማ የሚያስደንቅ ምሕረቱን በእኔ የገለጠ***
***እግዚአብሔር ይመስገን።***
[22]***እኔስ ከዓይንህ ፊት ተጣልሁ፥***
***በድንጋጤ አልሁ***
***አንተ ግን ወደ አንተ በጮኽሁ ጊዜ***
***የልመናዬን ቃል ሰማኸኝ።***

**31:19-22** ይህ አንጓ የሚገልጸው የያህዌን "መልካምነት" ነው (ቢዲቢ 375፣ መዝ. 145:7)። ምናልባት ይሄንን አንጓ መረዳት የሚቻለው ያህዌ የመዝሙረኛውን የጸሎት ጥያቄዎች ከመለሰ በኋላ ነው፣ በመዝሙሩ ላይ ቀደም ብለው የሚገኙት።

1. ያህዌን ለሚፈሩት የተከማቸ።
2. በያህዌ ለሚታመኑ የሆነ።
3. ያህዌ ሕዝቡን ይሸሽጋል
   ሀ. በእርሱ መገኛ ምሥጢራዊ ስፍራ
   ለ. በመጠጊያው/በድንኳኑ
4. ያህዌ ቸርነቱን ለመዝሙረኛው በድንቅ አድርጓል።
5. ያህዌ ልመናውን ሰምቷል።

**31:19 "በሰው ልጆች ፊት"** ያህዌ መከላከልንና መጠበቅን ብቻ አያደርግም፣ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ያለንን የተለየ ግንኙነት በጠላቶቻችን ፊት ያውቃል (መዝ. 23:5)።

**31:20** ምሥጢራዊው ስፍራ ውስጠኛው (ወይም በስተጀርባ) ያለው መጠለያ ነው የመቅደሱ/የማደርያው ድንኳን (መዝ. 27:5)። ይህ የተለየ ስፍራ ነበር የያህዌ አካላዊ መገኘት የሚገለጥበት (ማለትም፣ የኪዳኑ ታቦት)።

**31:21 "በተከበበ ከተማ"** ምንም እንኳ የዚህን መዝሙር ታሪካዊ መቼት (ስፍራ) ባናውቀውም፣ ይህ ሐረግ ዘይቤአዊ ይመስላል። እሱም ስለ ግለሰቡ ይገልጻል፣ በኃጢአተኞች፣ በክፉዎች፣ በውሸተኞች ሰዎች እንደተከበበ የሚሰማው።

ምንም እንኳ መዝሙረኛው የተተወ ቢመስለውም፣ ያህዌ እንደሚሰማውና፣ በእርሱ አንጻር እንደሚሠራ ያምናል።

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 213) ለዚህ ምንባብ ደረጃ "ሀ" ይሰጣል፣ "በሥቃይ ውስጥ፣" በተቃርኖ አእምቅ ውስጥ ቢገኝም።

ጄፒኤስኦኤ ይሄን ሐረግ የሚተረጉመው ያህዌ ለምን "መባረክ" እንደሚኖርበት ባሕርይ በመስጠት ነው፣ 31:22ሀ። እሱ ብርቱ እና የማይለወጥ ነው (ማለትም፣ "ብርቱ ምሽግ")። የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ጎዳግ ይሄንን የሚያያይዘው ከያህዌ "ጠንካራ ዐለት" "ምሽግ" "ቋጥኝ" (ማለትም፣ ዐለት) እና "ምሽግ" ጋር ነው፣ 31:2-3 ላይ (ገጽ 1316)።

**31:22 "እኔስ ከዓይህ ፊት ተጣልሁ"** የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 1316) ይሄንን ሐረግ የሚተረጉመው "ከመቅደስ መቅረት" በሚል ፍች ነው (ማለትም፣ 2 ዜና. 26:21፣ እዚያም ተመሳሳይ ሐረግ ጥቅም ላይ የዋለበት፣ ዑዚያ እንደ ለምጻም ወደ መቅደስ መሄድ ያልቻለበት)። የዚህ ግሥ የኒፋል መልኩ (ቢዲቢ 173፣ ኬቢ 202) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ በብኪ።

***መዝሙር ፡ 31:23-24***

[23]***ሁላችሁ ቅዱሳኑ፥ እግዚአብሔርን ውደዱት***
***እግዚአብሔር እውነተኞችን ይፈልጋል፥***

**ትዕቢተኞችንም ፈጽሞ ይበቀላቸዋል።**
**[24]በእግዚአብሔር የምታምኑ ሁላችሁ፥**
**በርቱ ልባችሁም ይጥና።**

**31፡23-24** በመዝሙራት ላይ እጅግ አዘውትሮ እንደሆነ የመጨረሻው አንጓ የሚሆነው

1. ማስጠንቀቂያ
2. ምክር
3. የማጠቃለያ ጸሎት

እዚህጋ ቁ. 2 ነው። የመጀመሪያዎቹ ግሦች የሁለቱ ቁጥሮች የብዙ ተተኳሪዎች ናቸው።

1. ያህዌን ውደድ — ቢዲቢ 12፣ ኬቢ 17፣ ቃል ተተኳሪ፤ ይህ ግሥ ዘወትር የሚጠቅሰው የያህዌን ፍቅር ወይም ነጠላ ቁጥር ሆኖ የዘማሪውን ፍቅር ነው
2. በርታ — ቢዲቢ 304፣ ኬቢ 302፣ ቃል ተተኳሪ፤ እሱም ተመሳሳይ ይከተለዋል፣ ቢዲቢ 54፣ ኬቢ 5፣ ሂፊል ተጽዕኗዊ (የዕብራይስጥ ትይዩነት)

**31፡23 "ቅዱሳኑ"** ይህ የሚያመለክተው ታማኝ ተከታዮችን ነው (መዝ. 30:4፤ 37:28፤ 50:5), መላእክትን ሳይሆን (መዝ. 29:1)።

▣ የሕይወት ልምድ (እና የከሕይወት ወዲያ ልምድ) የ

1. ታማኝ — ቢዲቢ 52 l
2. ትዕቢት አድራጊዎች — ቢዲቢ 793 l፣ ኬቢ 889፣ ቃል ቦዝ አንቀጽ አወቃቀር ቢዲቢ 144

ተቃርነዋል።

1. ተጠብቋል – ቢዲቢ 665፣ ኬቢ 718፣ ቃል ቦዝ አንቀጽ
2. ተካክሷል – ቢዲቢ 1022፣ ኬቢ 1521፣ ፔል ቦዝ አንቀጽ

**31:24** ምን ዓይነቱ ምክር ነው፣ ለሁሉም ታማኝ ተከታዮች (መዝ. 27:14፤ 37:34፤ 62:5፤ 130:5፤ ኢሳ. 25:9)!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙረኛው በእንደዚህ ዓይነቱ ችግር ውስጥ ለምን ሆነ?
2. የኃጢአትን አካላዊና ማኅበራዊ መዘዞች ዘርዝር።
3. "ኀፍረት"ን በብኪ ዐውድ አብራራ።
4. ቁጥር 21 በጥሬው ነው ወይስ ዘይቤአዊ?
5. በአንድ ግለሰብ የተጻፉ በርካታ መዝሙራት ለምን በተጠቃለለ መልኩ ይፈጸማሉ?

## መዝሙር 32
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የምሕረት ባርኮት እና በእግዚአብሔር መታመን<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር። ማስኪል | የይቅርባይነት ደስታ | ለፈውስ ምስጋና ማቅረብ | ንስሐ እና ይቅርታ | ቀጥተኛ የኃጢአት ፍቃድ |
| 32:1-2 | | | | |
| 32:3-7 | 32:1-2 | 32:1-2 | 32:1-2 | 32:1-2 |
| | 32:3-5 | 32:3-4 | 32:3-4 | 32:3-4 |
| | | 32:5 | 32:5 | 32:5 |
| 32:8-11 | 32:6-7 | 32:6-7 | 32:6-7 | 32:6-7 |
| | 32:8-9 | 32:8-9 | 32:8-9 | 32:8 |
| | | | | 32:9 |
| | 32:10-11 | 32:10-11 | 32:10-11 | 32:10 |
| | | | | 32:11 |

### **የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ሦስተኛው አንቀጽ*
4. *ወዘተርፈ*

### ***ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት***

*ሀ.* ከኤምቲ መግቢያ የተነሣ ብዙ ሊቃውንት የሚያምኑት ይህ መዝሙር፣ እንደ መዝሙር 51 የሚገልጸው የዳዊትን ኃጢአት ነው (ማለትም፣ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት ከቤርሳቤህ ጋር መፈጸምና፣ ኦርዮን መግደል፣ 2 ሳሙኤል 11)፣ መሸፈን (2 ሳሙኤል 12)፣ እና ይቅር መባል (ማለትም፣ ምንም እንኳ የኃጢአቱ መዘዝ ቤተሰቡን ቢያጠፋም)። ሮሜ 4:7-8 ላይ ጳውሎስ የጠቀሰው 32:1-2 (LXX) ዳዊትን እንደሚያመለክት ነው።

*ለ.* ይህ በርግጥ ይቻላል፣ ነገር ግን ሰፋ ያለ አንድምታና ዓላማ ያለው ነው (የቁ. 11 የብዙዎች)። ኃጢአትና መዘዙ በሰዎች ሁሉ የተለመዱ ናቸው (ሮሜ. 1:8-3:18)፣ የኪዳን ሰዎች እንኳ ቢሆኑ (ሮሜ. 7፤ 1 ዮሐንስ 1:5-10)።

*ሐ.* የመዝሙረኛውን ሥጋዊ ችግሮች፣ የእግዚአብሔር የምሕረት ድርጊቶች ኃጢአተኛውን የኪዳን ሰው በዓመጸው/ዓመጸዋ እንዲቆዩ አላደረገም (ዕብ. 12:7-13)። የኃጢአት መዘዞች አሉ፣ እግዚአብሔር ይመስገን፣ የምሕረት አምላክ እነርሱም ቢኖሩ እያስጓዘን ነው። ኃጢአት እንደበዛ፣ ጸጋው ደግሞ እንዲሁ በዝቷልና (ሮሜ. 5:20)።

መ. አንዱ ሊገልጽ ይችላል፣ የትኞቹ ሁነቶች፣ እና ጉዳዮች የባህሉ ማዕከላዊ እንደሆኑ፣ እሱን ለመግለጽ ጥቅም ላይ በዋሉት ቃላት ቁጥር። ግልጽ የሆነው እስራኤል የኪዳን ዓመጸኝነት የሚመለከተው መሆኑ ነው (1 ነገ. 8)፣ ከምሕረቱም ጭምር። ለኃጢአትና ለዓመጸኝነት ብዙ ቃላት አሉ።

ሠ. መዝሙር 31 እና መዝሙር 32 አንድ ላይ ተደርገው ሊሆን ይችላል፣ በአዘጋጅ ወይም በአጠናቃሪ፣ ሁለቱም ስለ ኃጢአት ሥጋዊ ውጤት በመግለጻቸው ሳቢያ (መዝ. 31:9-10፤ 32:3-4)።

ረ. አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 769) ስለ ተናጋሪዎቹ አስገራሚ ንድፈ-ሐሳብ ይሰጣል።
1. በዳዊትና በያህዌ መካከል የተደረገ ንግግር፣ በቤተ መቅደስ፣ ቁ. 1-2
2. ዳዊት ለያህዌ ሲናገር፣ የተሰበሰቡት ምዕመናን እያደመጡ፣ ቁ. 3-7
3. ካህኑ ዳዊትን ሲያናግረው፣ በያህዌ አኳያ፣ ቁ. 8-10
4. ዳዊት ለተሰበሰቡት ምዕመናን ሲናገር፣ ቁ. 11

ሰ. ይህ መዝሙር አጽንዖት የሚሰጠው
1. የሰዎችን ኃጢአተኝነት
2. የእግዚአብሔርን የምሕረት ባሕርይ
3. ኃጢአተኛው ሰው በቅዱሱ እግዚአብሔር ፊት እንዴት ተቀባይነትን እንደሚያገኝ (ማለትም፣ ንስሐ)

የጳውሎስ የመዝሙር 32፡1-2 አጠቃቀም፣ ሮሜ 4 ላይ፣ እዚያም የብኪ ምሳሌዎችን የሚያስረዳበት፣ "ጽድቅ በጸጋ በእምነት በኩል" (ሮሜ. 3፡21-31፤ ገላትያ 3፤ ኤፌ. 2፡8-9)፣ የሚገልጸው ዐውደ-ጽሑፉ እንደ ብኪ ምሳሌ መሆኑን ነው፣ ጭብጡ በአኪ የጎለበተውና ቅድሚያ የተሰጠው። አንዱ እንዴት ይቅር እንደሚባል ይህ ዋነኛ ነገር ነው፣ ምንም እንኳ የእዛ ይቅርታ መንገድ (ማለትም፣ የክርስቶስ ወንጌል) ባይጠቀስም። እሱ አሁንም ገና በግልጽ ያስታውቃል፣ ምሕረት የተሞላውን፣ ጸጋውን፣ ሊገኝ የሚችለውን የያህዌን መሐሪነት (ማለትም፣ "ተነሥቷል ተወግዷልም" እናም "ተከድኗል")።

ያህዌ ዳዊትን መማር ከቻለ፣ አንተንም ይምርሃል! በመናዘዝና በንስሐ ተቀበለው! ከዚያም በተስፋዎቹ ይቅርታ ቁም!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 32፡1-2**

**የዳዊት ትምህርት።**
**[1]መተላለፉ የቀረችለት**
**ኃጢአቱም የተከደነችለት ምስጉን ነው።**
**[2]እግዚአብሔር በደልን የማይቈጥርበት**
**በመንፈሱም ሽንገላ የሌለበት ሰው ምስጉን ነው።**

**32፡1** "የተባረከ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 80፣ መዝ. 1፡1፣ 26 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ከ45 ጊዜ ውስጥ፣ መዝሙራት ላይ) ተደጋጋሚ ነው፣ በጥበብ ጽሑፎች፣ ታማኝ ተከታዮችንም ይገልጻል።
1. ኢዮብ 5፡17፤ መዝ. 94፡12 — በሻዳይ የተገሠጸ
2. መዝሙር 1፡1 — በእግዚአብሔር ቃል ጥናት እና ርምጃ
3. መዝሙር 2:12 – በያህዌ መታመን
4. መዝሙር 32:1-2 – ኃጢአት ይቅር ተብሏል
5. መዝሙር 40:4፤ 84:12፤ ምሳ. 16:20 – በያህዌ ይታመናል
6. መዝሙር 41:1-3፤ ምሳ. 14:21 – ድሀን ያስባል
7. መዝሙር 80:6 – በያህዌ ይበረታል
8. መዝሙር 89:12 – ደስታን ያውቃል እናም በያህዌ ፍቃድ አኳያ ይራመዳል
9. መዝሙር 119:2 – እሱን በሙሉ ልቡ ይፈልገዋል፣ ምስክርነቱን ያስተውላል
10. መዝሙር 112:1፤ 128:1 – ያህዌን ይፈራል፣ በመንገዱም ይሄዳል
11. መዝሙር 146:5 – ያህዌ ረዳቱ ነው
12. ምሳሌ 3:13 – ጥበብን ያገኛል
13. ምሳሌ 8:32፣34 – ያህዌን ያደምጣል፣ መንገዱንም ይጠብቃል
14. ምሳሌ 28:14 – ያህዌን ይፈራል
15. ምሳሌ 29:18 – የያህዌን ሕግ ያከብራል

የዚህ መዝሙር የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ቁጥሮች ከLXX በጳውሎስ ተጠቅሰዋል፣ ሮሜ 4፡7-8 ላይ፣ በዳዊት ምሳሌው፣ እንደ ብጹዕ ሰው፣ ኃጢአቱ ይቅር ስለተባለለት።

የተለያዩ ቃላትን ተገንዘቡ፣ በያህዌ ላይ ማመጽን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉ (ዝከ. ቁ. 5)።
1. መተላለፍ – ቢዲቢ 833፣ ኬቢ 981፤ እሱም የሚገልጸው የእግዚአብሔር ፍቃድ የሆነውን ሆን ብሎ መስበር ነው (ማለትም፣ ኪዳን)

2. ኃጢአት – ቢዲቢ 308፣ ኬቢ 306፤ እሱም የሚገልጸው መሳትን ነው (ቢዲቢ 306) የተቀመጠ ዒላማን፣ በድጋሚም ባለማወቅ አይደለም፣ በራስ ፍቃድ እንጂ
3. በደል – ቢዲቢ 730፣ ኬቢ 799፤ የተሳሳተ ሥራ፣ ኃጢአት (ቁ. 1፣2፣3 አንድ ላይ ይከሰታል ዘጸ. 34:7፤ ሌዋ. 16:21፤ ኢዮብ 12:23፤ እዚህ፤ ኢሳ. 59:12፤ ሕዝ. 21:24፤ ዳን. 9:24)
4. መሳት – ቢዲቢ 941፣ ኬቢ 636፤ መሳት ማለት ነው፣ መታለል፣ መጭበርበር፣ (መዝ. 52:2፤ 101:7፤ 120:2-3)

የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ ይጠቅሳል፣ መዝሙረኛው ሆን ብሎ ተባዕታይ፣ አንስታዩን መቀየሩ (ሁለቱ) ፍጽምናን ለማሳየት (ገጽ 303)።

የያህዌ (ተገብሮ ቦዝ አንቀጾቹን ተገንዘብ) ይቅርታ የሚገለጸው ለኃጢአተኞች የተሰጠውን ጽድቅ ነው፣ በእግዚአብሔር ምሕረትና በእነርሱም ንስሐ መግባት ላይ በመመሥረት (ይህ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ ነው፣ የአስተዋጽዖ [ዝኪ. ቢዲቢ 362፣ ኬቢ 359፣ ዘፍ. 15:6፤ ሮሜ. 4:3፤ ገላ. 3:6])።

1. ይቅር ተብሏል ("ወደ ላይ ከፍ ተደርጎ ተወስዷል") – ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724፣ ቃል ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ፣ ዘጸ. 32:32፤ 34:7፤ ዘኍ. 14:18፣19፤ ሚኪ. 7:18፤ ተመሳሳይ ቃል አሉታዊ ተደርጓል ዘጸ. 23:21 ፤ኢያ. 24:19፤ ኢዮብ 7:21፤ ኢሳ. 2:9 ላይ
2. ተከድኗል (ማለትም፣ ከእይታ ውጭ ተደርጓል፣ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ ኢሳ. 38:17፤ 43:25፤ ሚኪያስ 7:19 ላይ) – ቢዲቢ 491፣ ኬቢ 487፣ ቃል ተገብሮ ቦዝ አንቀጽ

ውጤቱ ምንም ስተሽ/ተንኮል የሌለበት ሰው ነው (ዮሐንስ 1:47)። ይህ ማለት ኃጢአት የሌለበት ማለት አይደለም፣ ንስሐ የሚገባ እንጂ።

**32፡2 "ሰው"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል አዳም ነው (ቢዲቢ 9)። በዘፍጥረት ፊተኞቹ ክፍሎች (ዘፍጥረት 1-3) እሱ የሚያመለክተው አዳምን ነው፣ ዋነኛው የሰው ፍጥረት፣ ነገር ግን እሱ የሚወስደው የሰውነትን አጠቃላይ መልክ ነው።

**መዝሙር ፡ 32፡3-7**

**3 ሁልጊዜ ከመጮኼ የተነሣ**
**ዝም ባልሁ ጊዜ አጥንቶቼ ተበላሹ**
**4 በቀንና በሌሊት እጅህ ከብዳብኛለችና፥**
**እርጥበቴም ለበጋ ትኩሳት ተለወጠ። ሴላህ**
**5 ኃጢአቴን ለአንተ አስታወቅሁ፥**
**በደሌንም አልሸፈንሁም**
**ለእግዚአብሔር መተላለፌን እነግራለሁ አልሁ**
**አንተም የልቤን ኃጢአት ተውህልኝ።**
**6 ስለዚህ ቅዱስ ሁሉ በምቹ ጊዜ ወደ አንተ ይለምናል**
**ብዙ የጥፋት ውኃም ወደ እርሱ አይቀርብም።**
**7 አንተ ለእኔ መሸሸጊያዬ ነህ፥ ከጣርም ትጠብቀኛለህ**
**ከከበቡኝ ታድነኝ ዘንድ ደስታዬ ነህ። ሴላህ**

**32፡3-7** ይህ አንጓ ሁለት መንገዶችን ያቃርናል፣ ኃጢአትን በተመለከተ።

1. ዝም ማለት፣እሱን መደበቅ
   ሀ. አጥንቶች ይበላሻሉ፣ መዝ. 31፡9-10
   ለ. ቀኑን ሁሉ ይጮኻል
   ሐ. ጠቀሜታ ("ርጥበት፣" ቢዲቢ 545፣ ዘኍ. 11፡8፤ እዚህጋ ጥቅም ላይ የዋለው ለአካል ፈሳሾች ነው) ተቀድቶ አለቀ (አአት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው "ለጥፋቱ፣" የሚል ማስተካከያ ነው ገጽ 888 ቁ. 29)
2. እውቅና ይሰጣል፣ ይናዘዛል
   ሀ. ያህዌ የኃጢአትን በደል ይቅር ይላል (ዘጸ. 34:7፤ ዘኍ. 14:18፤መዝ. 85:2)
   ለ. የደኅንነት ስሜት ይመለሳል
   ሐ. ያህዌ በድጋሚ የመደበቂያ ስፍራ ነው
   መ. ያህዌ ከችግር ይጠብቀዋል
   ሠ. እሱ በመዳን መዝሙራት ተከብቧል

በያህዌ እጅ ላይ የቃላት መዘዋወር አለ፤ በፍርድ ላይ ይከብዳል (ቁ. 4፤ መዝ. 38:2፤ 39:10፤ ኢዮብ 23:2) ነገር ግን በንስሐ እሱ ይጠብቀዋል (ቁ. 6-7)።

**32፡4፣5፣7 "ሴላህ"** መዝ. 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ እና የመዝሙር VII መግቢያ ተመልከት።

**32፡5 "እናዘዛለሁ"** የስንኝ 1 እና 2 ትይዩነት የግሡን ያልፎ-አልፎ ፍች ይጠይቃል (ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ በኅብራዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ)። ዘወትር በሂፊል ያለው ግሥ ፍችው "ምስጋና ማቅረብ፣" ነው፣ ነገር ግን በጥቂት ዐውደ-ጽሑፎች "መናዘዝ" አጠቃላይ ፍችው ነው።

1. 1 ነገ. 8:33፣35፤ 2 ዜና. 6:24፣26 የሚጠቅሰው "የያህዌን ስም መመስከር"
2. እዚህና ምሳ. 28:13 ላይ ዐውደ-ጽሑፉ የሚጠቅሰው "ኃጢአትን መናዘዝ" ነው

**32:6 "አንተ በምትገኝበት ጊዜ"** ይህን አሻሚ ሐረግ በበርካታ መንገዶች መረዳት ይቻላል።

1. የተቀጠረ/ምቹ ጊዜ ለንስሐ ይኖራል (LXX፣ ቫልጌት፣ አኪጀት)
2. በችግር ወይም በመከራ ጊዜ መጸለይ (2 ዜና. 15:4፤ ማሻሻያ ዝከ. አየተመት፣ አእቅ፣ አኢመቅ)
3. ኤምቲ "በሚገኝበት ጊዜ" የሚል አለው (ምሳ. 103:8-14፤ ኢሳ. 55:6)። ጄፒኤስአኤ ይህንን የሚተረጉመው "በተደረሰበት ሰዓት [ኃጢአቱን] በሚል ነው።"

◘ **"ብዙ የጥፋት ውኃ"** ውኃ፣ የጎርፍ ውኃ፣ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው እንደ ችግር/መከራ/ጥቃት ዘይቤ ነው፣ መዝ. 69:1፤ 124:5፤ 144:7 እና እጅግ በተዋበ መልኩ ኢሳ. 43:2 ላይ)።

**32፡7** ይህ የማደሪያውን ድንኳን/መቅደስ የሚጠቅስ ነው። የምስጋና መዝሙራት የአምልኮ ዝማሬዎች ናቸው፣ ወይም የአምልኮ ሥነ-ሥርዓት።

**መዝሙር ፡ 32፡8-11**

**8 አስተምርሃለሁ በምትሄድበትም መንገድ እመራሃለሁ**
**ዓይኖቼን በአንተ ላይ አጠናለሁ።**
**9 ወደ አንተ እንዳይቀርቡ**
**በልባብና በልጓም ጕንጫቸውን እንደሚለጕሙአቸው፥**
**ልብ እንደሌላቸው እንደ ፈረስና እንደ በቅሎ አትሁኑ።**
**10 በኃጢአተኛ ብዙ መቅሠፍት አለበት**
**በእግዚአብሔር የሚታመነውን ግን ምሕረት ይከብበዋል።**
**11 ጻድቃን ሆይ፥ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ**
**ሐሤትም አድርጉ**

**32፡8-11** መዝሙረኛው ለራሱ ይናገራል (እና ለሌሎች፣ ቁ. 5) በያህዌ አኳያ። መለኮታዊው ምላሽ ይሄውና፣ ቁ. 8 (ሦስት ተጓዳኞች)!

1. ቁጥር 5፣ መተላለፌን እናዘዛለሁ – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ
   ጥቅም ላይ የዋለ (ሙሉ ማስታወሻውን ቁ. 5 ላይ ተመልከት)
2. ቁጥር 8፣ አስተምርህማለሁ – ቢዲቢ 968፣ ኬቢ 1328፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ
   ጥቅም ላይ የዋለ
   አስተምርህማለሁ – ቢዲቢ 434፣ ኬቢ 436፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   እመክርሃለሁ – ቢዲቢ 419፣ ኬቢ 421፣ *ቃል* በተጓዳኝ፣ መዝ. 16:7

**32፡8 "በመንገድ"** ይህ ለመልካም ሕይወት ፈሊጥ ነው (መዝ. 1:1፤ 25:8-9)።

◘ **"ዓይኖቼን በአንተ ላይ አጠናለሁ።"** ይህ ለግላዊ ክብካቤ እና መገኘት ፈሊጥ ነው (ዝከ. 32:18፤ መዝ. 34:15 [1 ጴጥ. 3:12 ላይ ተጠቅሷል]፤ ኢዮብ 36:7)።

ለ"ዓይን" ለያህዌ ጥቅም ላይ የዋለ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አምላክ እንደ ሰውኛ ሲገለጽ (ሰዋዊነት) መዝሙር 2፡4-6 ላይ።

**32፡9** ሰዉ (የብዙ ቁጥር) ንስሐ የማይገባው በዓመፀኝነት፣ በቤት እንስሳት መልኩ ነው የተገለጸው (ኢሳ. 1፡2-3)። የወደቀው ሰው የሚኖረው በእንስሳት ደረጃ ነው፣ ባሕርዩም "የሆነው ቢሆን ለእኔ ለእኔ ብቻ!" የሚል።

◘ በድኃሚ ተቃርኖ።

1. ኃጢአተኛ — ብዙ ኀዘን
2. ታማኝ ተከታይ (ማለትም፣ "ያህዌን የሚያምን")፣ የኪዳን ታማኝነትና ፍቅር ይከብበዋል (ዝከ. 32፡7ለ)

◘ **"ቸርነት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝሙር 5፡7 ላይ።

◘ **"ይከብበዋል"** *ግሡ* (ቢዲቢ 685፣ ኬቢ 738፣ *ፖል ያልተጠናቀቀ*) ደግሞ ቁ. 7 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ የመታደግ መዝሙር እና እዚህ ለያህዌ ቸርነት (ደግሞም ዘዳ. 32:10 እይ፤ ቅጽሉ መዝ. 34:7፤ 125:2) ላይ ጥቅም ላይ ውሏል። እንዴት ያለው ፈሊጥ ነው፣ የያህዌ መገኘትና ጥበቃ!

**32፡11** ተለጣጣቂ የብዙ ቁጥር ተተኳሪዎች፣ ታማኝ ተከታይን ለማስተማር።

1. ተደሰት – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. ሐሤት አድርግ – ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. በደስታ ጩኽ – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. አካላዊ ችግሮችን ዘርዝር፣ ካልተናዘዙት ኃጢአት ጋር የሚዛመዱትን። "መናዘዝ" ምን ማለት ነው?
2. መዝሙር 32 እና 51 እንዴት ይዛመዳሉ?
3. ቁጥር 6ሀ ምን ማለት እንደሆነ አስረዳ። የሚናዘዙበት ጊዜ ያልፍ ይሆን (ማለትም፣ የዕድል መስኮት)?
4. ቁጥር 8-9 ላይ ማነው የሚናገረው?

# መዝሙር 33
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ምስጋና ለፈጣሪና ለጠባቂ ኤምቲ መግቢያ የለውም | የጌታ ልዕልና በፍጥረትና በታሪክ | ውዳሴ ለአምላክ፣ ለፈጣሪ እና ለታሪክ ጌታ | የምስጋና መዝሙር | ውዳሴ ለጥበቃው |
| 33:1-5 | 33:1-3 | 33:1-3 | 33:1-3 | 33:1-3 |
| | 33:4-5 | 33:4-5 | 33:4-5 | 33:4-5 |
| 33:6-12 | 33:6-7 | 33:6-7 | 33:6-7 | 33:6-7 |
| | 33:8-9 | 33:8-9 | 33:8-9 | 33:8-9 |
| | 33:10-12 | 33:10-12 | 33:10-12 | 33:10-12 |
| 33:13-17 | 33:13-15 | 33:13-17 | 33:13-15 | 33:13-15 |
| | 33:16-17 | | 33:16-17 | 33:16-17 |
| 3:18-22 | 33:18-19 | 33:18-19 | 33:18-19 | 33:18-19 |
| | 33:20-22 | 33:20-22 | 33:20-22 | 33:20-22 |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 770) የሚለው ይህ መዝሙር የአምልኮ መሆኑን ነው።
1. የሌዋውያን ዘማርያን
   ሀ. መሪ፣ ቁ. 1-3
   ለ. ዘማርያን፣ ቁ. 4-19
2. የተሰብሳቢ ምዕመናን ምላሽ፣ ቁ. 22-23

ለ. እርሱ የኤምቲ ስም የለውም (እንደ መዝሙር 1፣ 2፣ 10)፣ ነገር ግን "አዲስ መዝሙር፣" ቁጥር 3 ላይ፣ የሚያመለክተው የሆነ ዋነኛ ታሪካዊ ሁነትን ነው። በቁ. 16-17 ምክንያት እሱ የሚያመለክተው ወታደራዊ ድል ነው።

ሐ. እኔ እገረማለሁ፣ በያህዌ ዓላማዎች ሁለንተናዊ ዳርቻ፣ እርሱም ሰዎችን ሁሉ የሚያካትተው (ማለትም፣ "ሁሉም" የሚለውን አጠቃቀም ተመልከት፣ 33:8፣ 13-15)። የቁ. 5ለ አስደንጋጩን ማረጋገጫ ተመልከት! ሙሉውን የጽሑፍ ዝርዝር ተመልከት፣ እሱም የአሕዛብን መካተት የሚያሳየውን፣ በያህዌ የመዳረሻ ዓላማ ኪዳን ላይ ከመጀመሪያው ጀምሮ እንደሆነ፣ በእኔ ማስታወሻ 33:10-12 ላይ።

**መዝሙር ፡ 33፡1-5**

**የዳዊት መዝሙር።**
**1ጻድቃን ሆይ፥ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ**
**ለቅኖች ምስጋና ይገባል።**
**2እግዚአብሔርን በመሰንቆ አመስግኑት፥**
**አሥር አውታርም ባለው በበገና ዘምሩለት።**
**3አዲስ ቅኔም ተቀኙለት፥**
**በእልልታም መልካም ዝማሬ ዘምሩ**
**4የእግዚአብሔር ቃል ቅን ነውና**
**ሥራውም ሁሉ በእምነት ነውና።**
**5ጽድቅንና ፍርድን ይወድዳል**
**የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች።**

**33፡1-5** *የመጀመሪያዎቹ ሦስቱ ቁጥሮች የመዝሙሩን ሁኔታ ያበጃሉ፣ እግዚአብሔርን ለማመስገን (ማለትም፣ አምስት ትይዩ ተተኳሪዎች)።*

1. ለእግዚአብሔር በደስታ ዘምሩ – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ *ፔል ተተኳሪ (ይኸው ተመሳሳይ ግሥ መዝሙር 32ን ያጠቃልላል)*
2. ምስጋና – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
3. ለእርሱ ምስጋና ዘምሩ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ *ፔል ተተኳሪ*
4. ለእርሱ ዘምሩ – ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ *ቃል ተተኳሪ*
5. *መልካም ዝማሬ ዘምሩ (ቢዲቢ 618፣ ኬቢ 668፣ ፔል ያልተወሰነ አወቃቀር) በደስታ ዕልልታ* – ቢዲቢ 405፣ ኬቢ 408፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

ቁጥር 4 እና 5 ለምስጋናው ምክንያት ይሰጣል።

1. የያህዌ ቃል (ቢዲቢ 182) ቀና ነው (ቢዲቢ 449)
2. የእርሱ *ሥራዎች* ሁሉ የሚከወኑት በታማኝነት ነው (ቢዲቢ 53፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት *መዝ.* 12፡1 ላይ)
3. እሱ ጽድቅን ይወዳል (ቢዲቢ 842፣ *መዝ.* 1፡5 ላይ ልዩ ርዕስ ተመልከት) እና ፍርድን (ቢዲቢ 1048፣ *መዝ.* 9፡5-6 ልዩ ርዕስ ተመልከት)
4. ምድር የእግዚአብሔርን ቸርነት ተሞልታለች (ቢዲቢ 338፣ *መዝ.* 119:64፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት *መዝ.* 5፡7 ላይ

የሰላምና ደኅንነት ቁልፍ የታማኝ ተከታዮች እምነትና መታመን ነው፣ በማይለወጠው፣ በመሐሪው፣ በጸጋ ባሕርዩ በኪዳን *መሥራቹ* አምላክ ላይ (*መዝ.* 102:27፤ ሚል. 3:6፤ *ዕብ.* 13:8)! የመጽሐፍ ቅዱስ ዐቢዩ ገጸ-ባሕርይ እግዚአብሔር ነው! እሱ የእርሱ *ታሪክ* ነው! እሱ የእርሱ ዕቅድና ዓላማ ነው!

**33፡2** ሁለት የአውታር (ክር) *መሣርያዎች* ተጠቅሰዋል።

1. *መሰንቆ* (ቢዲቢ 490) — *ይህ ሁለት ወይም አራት ክሮች ይኖሩታል።* እሱም በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) በስፋት ጥቅም ላይ ይውል ነበር። ይህም፣ ዳዊት ለንጉሥ ሳኦል የሚጫወትበት ነበር፣ የመንፈስ ጥንካሬ እንዲያገኝ (1 ሳሙ. 16፡16)።
2. በገና ባለ አስር አውታር (ቢዲቢ 614 አወቃቀር ቢዲቢ 797)። እሱም የ*መሣርያዎች* ምድብ ክፍል ነው፣ በሁለቱም በዓለማዊ እና በአምልኮ መቼት ጥቅም ላይ የሚውል (1 ሳሙ. 10፡5)።

▣ **"አዲስ *ዝማሬ*"** የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ሕዝቦች መዝሙርን የሚጽፉት ዋነኞቹን ሁነቶችና ሰዎች ለማስታወስ ነበር (ዘጸአት 15፤ 1 ሳሙኤል 22)። እዚህ ግለሰቡ ያህዌ ነው፣ ፈጣሪው (*መዝ.* 40:3፤ 96:1፤ 98:1፤ 144:9፤ 149:1፤ ኢሳ. 42:10፤ *ራዕ.* 5:9፤ 14:3)።

**መዝሙር ፡ 33፡6-12**

**6በእግዚአብሔር ቃል ሰማዮች ጸኑ፥**
**ሠራዊታቸውም ሁሉ በአፉ እስትንፋስ**
**7የባሕርን ውኃ እንደ ረዋት የሚሰበስበው፥**
**ቀላዮችንም በመዝገቦች የሚያኖራቸው።**
**8ምድር ሁሉ እግዚአብሔርን ትፍራው፥**
**በዓለም የሚኖሩ ሁሉም ከእርሱ የተነሣ ይደንግጡ።**
**9እርሱ ተናግሮአልና፥ ሆኑም**

እርሱ አዘዘ፥ ጸኑም።
10 እግዚአብሔር የአሕዛብን ምክር ያጠፋል፥
የአሕዛብንም አሳብ ይመልሳል።
11 የእግዚአብሔር ምክር ግን ለዘላለም ይኖራል።
የልቡም አሳብ ለልጅ ልጅ ነው።
12 እግዚአብሔር አምላኩ የሚሆንለት ሕዝብ ምስጉን ነው፥
እርሱ ለርስቱ የመረጠው ሕዝብ።

**33፡6-12** ይህ አንጓ ሁለት ዋነኛ እውነቶች አሉት።

1. ያህዌ ፈጣሪ ነው፣ ቁ. 6-9 (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አህዳዊነት፣ መዝ. 2፡7 ላይ)
2. ያህዌ ለአሕዛብ ዓላማ አለው፣ ቁ. 10-12 (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)

**33፡6 "የእግዚአብሔር ቃል"** ይህ በርግጠኝነት የሚያንጸባርቀው ዘፍጥረት 1-2 (መዝሙር 104) ነው። በቀጥታ መስመር www.freebiblecommentary.org ዘፍጥረት 1-2 ላይ ያለውን ትርጓሜያዊ ሐተታ ጊዜ ወስዳችሁ እንደምትመለከቱት ተስፋ አለኝ።

በዕብራይስጥ አስተሳሰብ፣ ፍጥረት ከምንም ነው (*ex nihilo*) በንግግር ቃል (*fiat*፣ መዝ. 33፡9፤ ዘፍጥረት 1፤ መዝ. 148፡5፤ 2 ቆሮ. 4፡6፤ ዕብ. 11፡3)። የእግዚአብሔር ቃል ፈሊጥ ነው፣ ለእግዚአብሔር ሐሳብ ወይም ፍቃድ። ዘመናዊዎቹ አማኞች በብዙ ጉዳዮች ላይ ይጋጫሉ፣ ከዘፍጥረት 1-2 ጋር በተያያዘ። የጆን ዋልተን አዲስ መጽሐፍ፣ *የዘፍጥረት አንዱ የጠፋው ዓለም*፣ ለእኔ ብዙ በረከት ሆኖልኛል፣ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ስታገል።

▣ **"ሰማያት"** ይህ የሚያመለክተው ከምድር በላይ ያለውን ከባቢ ዓየር ነው። የጥንቶቹ የሚመለከቱት እንደ ጠጣር ክዳን ነው፣ የተዘረጋ ቆዳ፣ ለዝናብ መስኮቶች እንዳሉት። መጽሐፍ ቅዱስ "ጸረ-ሳይንሳዊ" አለመሆኑን አስታውሱ፣ "ቅድመ-ሳይንሳዊ" እንጂ። እሱም ነገሮችን ይገልጻል፣ በአምስቱ የስሜት ሕዋሳት፣ በሚከሰቱበት አግባብ (ማለትም፣ ክስተታዊ ቋንቋ)። ከዘመናዊ ምዕራባዊ ጥሬ ትርጓሜ ተጠንቀቁ። መጽሐፍ ቅዱስ ጥንታዊ ምስራቃዊ መጽሐፍ ነው! መጽሐፍ ቅዱስ በጊዜው የእግዚአብሔር ቃል መሆን አለበት፣ ለእኛ ጊዜ የእግዚአብሔር ቃል ከመሆኑ በፊት።

ለመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ተገቢ መርሖዎች ጉዳይ የሚያስብዎት ከሆኑ የእኔን የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ሴሚናር ይመልከቱ (ቪዲዮ፣ የድምጽ፣ የተጻፈ መጽሐፍ) www.freebiblecommentary.org ላይ።

▣ **"ሠራዊታቸውም ሁሉ"** ይህ የሚያመለክተው የዚህን ዓለም የተጠናቀቀ ፍጥረት ነው (ዘፍ. 2፡1)። የጥንቶቹ ሰማያዊዎቹን ብርሃናት የሚመለከቱት (ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ፕላኔቶች፣ ተወርዋሪ ከዋክብት) በጠፈር ላይ እንደሚሽከረከሩ ነው። እነርሱ አማልክት አይደሉም፣ ነገር ግን የያህዌ የተዋበ ሥጋዊ ፍጥረት ክፋይ እንጂ። ዘፍጥረት 1 ከሥነ-መለኮት አኳያ አገልግሎት አለው፣ የባቢሎናውያንን አማልክት ለማንኳሰስ፣ ልክ የዘጸአት 7-11 መቅሠፍቶች የግብፃውያንን አማልክት ለማንኳሰስ ጥቅም ላይ እንደዋሉ።

**33፡7** "የውኃዎች" ርዕሰ-ጉዳይ በርካታ ገጽታዎች አሉት።

1. ዘፍጥረት ለይቶ እግዚአብሔር ውኃን እንደፈጠረ አይጠቅስም።
2. በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አፈ-ታሪክ ጨውማ ውኃና ንጹሕ ውኃ አማልክት ነበሩ። ያህዌ አሸነፋቸው!
3. ውኃ የያህዌ የፍርድ መሣርያ ሆኗል፣ እናም በድጋሚ በኖኅ ጀምሯል (ዘፍጥረት 6-9)።
4. ውኃ ለጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ሕዝቦች ዋነኛ ነገር ነበር። እነርሱ የርቢ አምልኮ ጀምረው ነበር፣ የተፈጥሮን መደበኛ ዑደት ለማረጋገጫ መንገድ (ማለትም፣ ዝናብ በወቅቱ)።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **የተእመቅ** | **"እንደ ክምር"** |
| **አአመመቅ ኅዳግ** | **"በውኃ አቁማዳ"** |
| **አየተመት** | **"እንደ ጠርሙስ"** |
| **አኢመቅ** | **"እንደ ግድብ"** |
| **LXX** | **"እንደ ወይን አቁማዳ"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"እንደ ክምር"** |

ኤምቲ "ክምር" የሚል አለው (ቢዲቢ 622፣ נד ፣ ዘጸ. 15፡8፤ ኢያ. 3፡13፣16፤ መዝ. 78፡13)። እሱም ዘፍ. 1፡9ን የሚጠቅስ ይመስላል። የዩቢኤስ ጽሑፍ ፕሮጀክት "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል፣ (ማለትም፣ መጠነኛ አጠራጣሪነት)።

የአአመመቅ ኅዳግ፣ አየተመት፣ LXX የሚወስዱት ከተለየ ሥር ነው፣ ቢዲቢ 609 (ኢያ. 9፡4፣13፤ መሳ. 4፡19፤ መዝ. 56፡8፤ 119፡83)።

የአጋድያንና ዑጋሪታዊ ሥር አለ፣ נאד፣ ፍችውም "ማሰሮ" ወይም "ጠርሙስ።"

**33፡8** ይህ ቁጥር የሚጀምረው በሁለት ቁጥሮች ነው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ (ማለትም፣ "እን...)።

1. ምድር ሁሉ ያህዌን ትፍራ/ታክብር (ቢ.ዲ.ቢ. 431፣ ኬ.ቢ. 432፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*፣ መዝ. 67:7)
2. በምድር የሚኖሩ ሁሉ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:2 ላይ) በድንጋጤ ይቁሙ (ቢ.ዲ.ቢ. 158፣ ኬ.ቢ. 185፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) ከእርሱ የተነሣ

ትይዩነቱን ተገንዘብ። ያህዌ መፈራት ይኖርበታል፣ ተፈጥሮ ሳይሆን። ዛሬ የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት ጠላት፣ በምዕራባዊው ኅብረተሰብ "ተፈጥሯዊነት" ነው፣ ወኪል-የለሽ፣ ዓላማ-የለሽ ዩኒቨርስ።

**33፡9** ቁጥር 6 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**33፡10-12** ሥነ-መለኮታዊው ማስረገጫ፣ ከሥጋዊው ፍጥረት ጋር የተያያዘው፣ አሁን የሚያተኩረው በዛ ፍጥረት ዓላማ ላይ ነው፣ እሱም ከፈጣሪ ጋር ኅብረት (ዘፍ. 1:26፣27፤ 3:8)።

"ሕዝቦች" (ማለትም፣ አሕዛብ) ሁለተኛ ሐሳብ አይደሉም ነገር ግን ከመጀመሪያውም የያህዌ ሐሳብ ናቸው እንጂ (ዘፍ. 3:15፤ 12:3፤ ዘጸ. 19:5፤ መዝ. 22:27፤ 66:1-4፤ 86:8-10፤ ኢሳ. 2:2-4፤ 12:4-5፤ 25:6-9፤ 42:6-12፤ 45:22-23፤ 49:5-6፤ 51:4-5፤ 56:6-8፤ 60:1-3፤ 66:23፤ ሚኪያስ 4:14፤ ሚል. 1:11፤ ዮሐንስ 3:16፤ 4:42፤ ሐዋ. 10:34-35፤ 1 ጢሞ. 2:4፤ ቲቶ 2:11፤ 2 ጴጥ. 3:9፤ 1 ዮሐንስ 2:1፤ 4:14)። ልዩ ርዕስ ተመልከት: የቦብ ወንጌላዊነት ቅድመ-አቋሞች፣ መዝሙር 2 መግቢያ ላይ።

**33፡10 "ምክር"** "ምክር (ቢ.ዲ.ቢ. 420፣ ማለትም፣ ዓላማ) የጌታ ለዘላለም ትቆማለች" (ኢዮብ 23:13፤ ምሳ. 19:21)። አሜን!

**33፡12** እግዚአብሔር ለደኅንነት የመረጠው ጥቂቶቹን ነው ወይስ ሁሉንም? ይህ አስቸጋሪ ጥያቄ ነው፣ ለእግዚአብሔር ሉዓላዊነት አልያም ለሰው ነጻ ፍቃድ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምርጫ/ዕጣ-ፈንታ እና የሥነ-መለኮት ሚዛን አስፈላጊነት፣ መዝ. 25፡12 ላይ።

የያህዌ ፍቅር፣ ዕቅድ፣ እና ዓላማ ያካትታል፣ ነገር ግን ከአብርሃም ዘሮች ይተልቃል! እሱ ሁሉም እንዲያውቁት ይፈልጋል (ከላይ ያለውን የቅዱስ ቃሉን ጽሑፎች ዝርዝር ተመልከት)!

***መዝሙር ፡ 33፡13-17***

**13 እግዚአብሔር ከሰማይ ተመለከተ፥**
**የሰውንም ልጆች ሁሉ አየ።**
**14 ከማደሪያው ቦታ ሆኖ**
**በምድር ወደሚኖሩ ሁሉ ተመለከተ፥**
**15 እርሱ ብቻውን ልባቸውን የሠራ**
**ሥራቸውንም ሁሉ የሚያስተውል።**
**16 ንጉሥ በሠራዊቱ ብዛት አይድንም**
**ኃያልም በኃይሉ ብዛት አያመልጥም።**
**17 ፈረስም ከንቱ ነው፥ አያድንም**
**በኃይሉም ብዛት አያመልጥም።**

**33፡13-17** ይህ አንጓ የሚያተኩረው በያህዌ ወሰን-የለሽነት ላይ ነው (መዝ. 14:2፤ 102:19)። እሱ በምድር ላይ የሚሆነውን ያውቃል፣ በሰዎች ሕይወት ላይ (ዘጸ. 3:7-9፤ ማቴ. 6:25-34፤ 10:30፤ ሉቃስ 21:18፤ ሐዋ. 27:34፤ ይኸው ተመሳሳይ ምስያ በበርካታ የብኪ ጽሑፎች ላይ ይገኛል፣ ማለትም፣ 1 ሳሙ.14:45፤ 2 ሳሙ. 14:11፤ 1 ነገ. 1:52)። የታማኝ አገልጋዮች ሕይወት በዕድል፣ በአጋጣሚ፣ በዕጣ-ፈንታ ቁጥጥር ሥር አይደለም፣ ነገር ግን የሚመራው በእምነት ነው፣ በእግዚአብሔር! ለእርሱ በግልጽ ኑሩ!

"ሁሉም" ምን ያህል ጊዜ እንደተከሰተ ተገንዘቡ (ቢ.ዲ.ቢ. 481) በዚህ መዝሙር ላይ፣ 33፡8ሀ፣ለ፣13ለ፣ 14ለ፣ 15ሀ፣ለ። ያህዌ ፈጥሯል፣ እናም ሁሉንም ሰብዓዊ ፍጡር ይገነዘባል! ሕይወት ዓላማ ያለው ስጦታ ነው። ሰዎች ሁሉ ለእግዚአብሔር ምላሽ ይሰጣሉ፣ ለእዛ ስጦታ መጋቢነታቸው!

**33፡15** ያህዌ ሰዎችን ሁሉ ሠርቷል (ቢ.ዲ.ቢ. 427፣ ኬ.ቢ. 428፣ *ቃል አንቀጽ*፣ ዘፍ. 2:7፣8፣19) ሕይወታቸውንም ያውቃል (መዝሙር 139)። እሱ ተገቢ ፈራጅ ነው፣ ምክንያቱም ፍቃዳችንን፣ ሐሳባችንን፣ ድርጊታችንን፣ እና ውጤቱን ስለሚያውቅ (ስለዚህ ርዕሰ-ጉዳይ ሙሉውን የጽሑፍ ዝርዝር፣ መዝሙር 28፡4 ላይ ተመልከት)።

**33፡16-17** የሰው ሁነቶች፣ ታሪክ፣ የአጋጣሚ አይደለም፣ ነገር ግን ዓላማ ያለው እንጂ። ያህዌ ለዓላማው ክፉውን እንኳ ይጠቀማል። ነገሮች እንዲያው አይሆኑም! እንግዲህ፣ ፍትሐዊ ለመሆን፣ ይህ የወደቀ ዓለም ነው፣ እናም የሚከሰተው ሁሉ የእግዚአብሔር ፍቃድ አይደለም። እሱ ይፈቅዳል፣ ምርጫዎቻችን ፍሬ ያፈሩ ዘንድ (ማለትም፣ መልካም ወይም ክፉ)። ምድር በሰው ልጅ ኃጢአት ተጎድታለች (ዘፍጥረት 3፤ ኢሳ. 53፡6፤ ሮሜ. 8፡18-23)። ምሥጢሩ እንዴት ነው

1. የያህዌ ሉዓላዊነት
2. የሰው ምርጫዎች
3. የሥጋዊ ድርጊት ኅብራዊ አሠራር

የእምነት ዓይኖች በሁሉም ሁነቶች ላይ እግዚአብሔርን ይፈልጋሉ (ዝኪ. ቁ. 18-22)። ክፉው ኃይልን፣ ሀብትን፣ ክፉዎችን፣ ጥፋቶችን እና አጋጣሚዎችን የሚፈልገው ለግሉ ነው! ሰዎች በወታደራዊ ኃይል ተስፋ ማድረግ አይኖርባቸውም (መዝሙር 2)።

> **መዝሙር ፡ 33፥18-22**
>
> **18 እነሆ፥ የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደሚፈሩት ናቸው፥**
> **በምሕረቱም ወደሚታመኑ፥**
> **19 ነፍሳቸውን ከሞት ያድን ዘንድ፥**
> **በራብም ጊዜ ይመግባቸው ዘንድ።**
> **20 ነፍሳችን እግዚአብሔርን ተስፋ ታደርገዋለች፥**
> **ረዳታችንና መጠጊያችን እርሱ ነውና።**
> **21 ልባችን በእርሱ ደስ ይለዋልና፥**
> **በቅዱስ ስሙም ታምነናልና።**
> **22 አቤቱ፥ ምሕረትህ በላያችን ትሁን፥**
> **በአንተ እንደ ታመንን።**

**33፥18-22** ታማኝ ተከታዮች ባሕርያቸው ምን እንደሆነ ተገንዘብ።

1. ያህዌን የሚፈሩ፣ ቁ. 18
2. የእርሱን ቸርነት ተስፋ የሚያደርጉ፣ ቁ. 18
3. ያህዌን የሚጠብቁ፣ ቁ. 20
4. እሱን እንደ ረዳታቸውና ጋሻቸው የሚመለከቱ፣ ቁ. 20
5. በእርሱ ደስ የሚላቸው፣ ቁ. 21
6. በእርሱ ቅዱስ ስም የሚታመኑ፣ ቁ. 21
7. በእርሱ ተስፋ የሚያደርጉ ("መጠበቅ") ቁ. 22

ያህዌም

1. ዓይኑን በእነርሱ ላይ ያደርጋል፣ ቁ. 13-15
2. ያድናቸዋል (ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ ሂፊል ያልተወሰነ አወቃቀር)
3. ይጠብቃቸዋል (ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ ፔል ያልተወሰነ አወቃቀር)
4. ይረዳቸዋል (ቢዲቢ 740) ይከላከልላቸዋል (ቢዲቢ 171)

በአብዛኞቹ መዝሙራት ማጠቃለያ ላይ የብዙ ቁጥር ጥቅም ላይ መዋሉን ተገንዘብ፣ ጸሎት/ምስጋናውን ከአንድ ወደ ሁሉም ታማኝ ተከታዮች ለማስፋት።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ቁጥር 1-3 ላይ ያሉትን ተተኳሪዎች ዘርዝር፣ ከዜማ አምልኮ ጋርም አዛምዳቸው። ዜማ ይሄን ያህል የአምልኮ ጠቃሚ ገጽታ የሆነው ለምንድነው?
2. ቁጥር 6-9 ዘፍጥረት 1ን እንዴት ያንጸባርቃል?
3. ቁጥር 11ን በገዛ ራስህ ቃላት አብራራ።
4. ቁጥር 15 እንዴት ዘፍ. 1፡26-28ን ያንጸባርቃል?
5. ያህዌ "ዓይን" አለውን?

## መዝሙር 34
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ ሰጭው እና ታዳጊው<br><br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>የዳዊት መዝሙር በአቤሜሌክ ፊት እንደ ዕብድ ሲቀየር፣ እሱም አስወጥቶት ራቀ | በአምላክ የሚታመኑት ደስታ | ከችግር በመዳን ምስጋና ማቅረብ (መስቀልያ) | ለእግዚአብሔር መልካምነት ምስጋና | ምስጋና ለእግዚአብሔር ፍርድ (መስቀልያ) |
| | | | | 34:1 (*ሐሴፍ*) |
| 34:1-3 | 34:1-3 | 34:1-3 | 34:1-3 | 34:2 (*ቤት*) |
| | | | | 34:3 (*Gimel*) |
| | | | | 34:4 (*Dalet*) |
| 34:4-7 | 34:4-7 | 34:4-10 | 34:4-7 | 34:5 (*He*) |
| | | | | 34:6 (*Zain*) |
| | | | | 34:7 (*Het*) |
| | | | | 34:8 (*Tet*) |
| 34:8-14 | 34:8-10 | | 34:8-10 | 34:9 (*Yod*) |
| | | | | 34:10 (*Kaph*) |
| | | | | 34:11 (*Lamed*) |
| | 34:11-14 | 34:11-14 | 34:11-14 | 34:12 (*Mem*) |
| | | | | 34:13 (*Nun*) |
| | | | | 34:14 (*Samek*) |
| | | | | 34:15 (*Ain*) |
| 34:15-18 | 34:15-16 | 34:15-18 | 34:15-18 | 34:16 (*Pe*) |
| | | | | 34:17 (*Zade*) |
| | 34:17-18 | | | 34:18 (*Qoph*) |
| | | | | 34:19 (*Resh*) |
| 34:19-22 | 34:19-22 | 34:19-22 | 34:19-21 | 34:20 (*Shin*) |
| | | | | 34:21-22 (*Taw*) |
| | | | 34:22 | |

### የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### *ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት*

*ሀ.* ይህ መስቀልያ መዝሙር ነው። እያንዳንዱ ቁጥር (ከቁጥር 5 በስተቀር፣ እሱም ሁለት የዕብራይስጥ ፊደላት ያሉት) በቅደም ተከተላዊ ፊደላት ነው የሚጀምረው፣ በዕብራይስጥ ፊደላት፣ 22 ፊደላት።
አስገራሚ የሚሆነው መስቀልያ ግጥም ከ22 ፊደላት በላይ ከሄደ ቀጣዩ ፊደል መደበኛ *Pe* ፒ መሆኑ ነው።

ለ. ለመስቀልያ መልኩ ብዙ ምሳሌዎች አሉ።
1. መዝሙር 9-10 (ግን ያልተጠናቀቀ፣ ሁለት ተናባቢዎች የሉም፣ ሁለቱ ደግሞ ተገልብጠዋል)
2. መዝሙር 25 (አንድ ተናባቢ የለም)
3. መዝሙር 34 (አንድ ቁጥር ሁለት ተናባቢዎች አሉት)
4. መዝሙር 37 (እያንዳንዱ ሁለት ቁጥር የሚጀምረው በቅደም ተከተላዊ ፊደላት ነው)
5. መዝሙር 111 (ሁለት ተናባቢዎች ለእያንዳንዱ ቁጥር)
6. መዝሙር 112 (ሁለት ተናባቢዎች ለእያንዳንዱ ቁጥር)
7. መዝሙር 119 (ስምንት ቁጥሮች ለእያንዳንዱ ተከታታይ ተናባቢ)
8. መዝሙር 145 (አልተጠናቀቀም)

ሐ. ያህዌ (ማለትም፣ ጌታ) ከሞላ ጎደል በእያንዳንዱ ቁጥር ላይ መከሰቱን ተገንዘብ። መዝሙሩ ስለ ያህዌ ነው። ሰዎች እሱን ያውቁታል፣
1. በድርጊቱ (ነህምያ 9)
2. በተስፋዎቹ (በተለይ፣ ዘፍጥረት 12፤ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)
3. በኪዳኑ (ዘፍጥረት — ዘዳግም)
4. በልጁ (ዮሐንስ 1:1-14፤ ቆላ. 1:13-16፤ ዕብ. 1:2-3)

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 34:1-3**
**ባሳደደው በአቤሜሌክ ፊት መልኩን በለወጠ ጊዜ በሄደም ጊዜ የዳዊት መዝሙር።**
**1 እግዚአብሔርን ሁልጊዜ እባርከዋለሁ፥**
**ምስጋናውንም ዘወትር በአፌ ነው።**
**2 ነፍሴ በእግዚአብሔር ትከብራለች፥**
**ገሮችም ሰምተው ደስ ይላቸዋል።**
**3 እግዚአብሔርን ከእኔ ጋር ታላቅ አድርጉት፥**
**በአንድነትም ስሙን ከፍ ከፍ እናድርግ።**

**34:1-3** ይህ የምስክርነት አንጓ ነው። እሱም በነጠላ ኅብራዊ ይጀምርና በብዙ ይጨርሳል። ያህዌ እጅግ ታላቅ ነው አስደናቂም፣ በባሕርዩ እና በድርጊቱ፣ እንዳይመሰገን!
1. ያህዌን እባርካለሁ – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ ፔል ኅብራዊ፣ ነጠላ
2. ስሙን ከፍ እናድርግ – ቢዲቢ 926፣ ኬቢ 1202፣ ፖለል ኅብራዊ፣ የብዙ

የምስጋናውን ባሕርይ ተገንዘቡ።
1. በሁሉም ጊዜያት — ይህ ጠቃሚ ማስታወሻ ነው፣ ያህዌ በመልካምም ሆነ በክፉ ጊዜያት መመስገን እንደሚኖርበት፤ እሱ አይለወጥም። የእርሱ ምሕረት ዘወትር ይኖራል! የእኛ አስተሳሰብ ብቻ ነው የሚቀየረው። እምነት መቀጠል ይኖርበታል፣ የእርሱን መገኘትና ምስጋና ለማጽናት፣ 1 ተሰ. 5:16-18።
2. ያለማቋረጥ (ቢዲቢ 556፣ መዝ. 35:27፤ 40:16፤ 70:4፤ 71:6) በአፌ — ምስጋና በግል ሁኔታዎች ላይ አይንተራስም፣ ነገር ግን የጸጋው ተቀባዮች ተገቢ ድርጊት መሆን ይኖርበታል።
3. ምስጋና ከሰዎች ሁሉ መነሣት አለበት (ማለትም፣ ትሑት፣ "የተቸገረ፣" "ምስኪን፣" ወይም "ደካማ" ቢዲቢ 776)። ሰዎች ሁሉ ብዙ ምክንያት ይኖራቸዋል፣ እግዚአብሔርን ለማመስገን!
4. በአንድነት — ምስጋና በሁለቱም ነው፣ በግለሰብም በአንድነትም (ማለትም፣ በአንድነት ቢዲቢ 403)፣ አምልኮት እንደሚሆነው። ግለሰባዊ መሻታችንን ወደ እርሱ እናመጣለን፣ እንዲሁም "የአንድነት መሻታችንን።" አንድነት እና ኅብረት በታማኝ ተከታዮች መካከል፣ ለእግዚአብሔር ምስጋና ያሳያል፣ እንዲሁም ለሌሎች ምስክርነት!

**34:2 "መመካት"** የዕብራይስጡ ግሥ (ቢዲቢ 237 II፣ ኬቢ 248፣ ሂዝፔል ያልተጠናቀቀ)፣ በሂዝፔል ማለት "መመካት፣" "ከፍ ማድረግ፣" ወይም "መመስገን" ነው (1 ነገ. 20:11፤ 1 ዜና. 16:10፤ መዝ. 64:11፤ 105:3፤ 106:5፤ ምሳ. 20:14፤ 25:14፤ 27:1፤ ኢሳ. 41:16፤ 45:25፤ ኤር. 9:23)።

ስለ “መመካት” ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መመካት መዝ. 20፡7 ላይ።

**34፡3 “እግዚአብሔርን ታላቅ አድርጉት”** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 152፤ ኬቢ 178፤ ፔል ተተኳሪ) ትዕዛዝ ነው፣ ለእግዚአብሔር የልባችንን አክብሮት ከምስጋናችን ጋር የምንገልጽበት። ለሕይወት ድካም እምቢተኝነታችንን ወይም በአሁኑ ሁኔታ ያለውን አስቸጋሪነት ከመግለጻችን በፊት ለራሳችን ማስታወስ ይኖርብናል

1. እግዚአብሔር ማን እንደሆነ
2. እሱ ምን እንዳደረገ
3. እሱ ምን እያደረገ እንደሆነ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 34፡4-7**

**[4]እግዚአብሔርን ፈለግሁት መለሰልኝም፥**
**ከመከራዬም ሁሉ አዳነኝ።**
**[5]ወደ እርሱ ቅረቡ ያበራላችሁማል፥**
**ፊታችሁም አያፍርም።**
**[6]ይህ ችግረኛ ጮኸ፥ እግዚአብሔርም ሰማው፥**
**ከመከራውም ሁሉ አዳነው።**
**[7]የእግዚአብሔር መልአክ በሚፈሩት ሰዎች ዙሪያ ይሰፍራል፥**
**ያድናቸውማል።**

**34፡4-7** ይህ አንጓ የመጀመሪያውን ሐሳብ ያጎለብታል። እሱም ከነጠላ (ማለትም፣ እግዚአብሔርን አየሁት) ወደ ብዙ እንዴት እንደሚሸጋገር ተገንዘቡ፣ (ማለትም፣ ወደ እርሱ ተመለከቱ)፣ ልክ እንደ መጀመሪያው አንጓ።

1. ለመዝሙረኛው፣ ያህዌ
   ሀ. መልሶለታል — ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ ቃል የተጠናቀቀ
   ለ. ከፍርሃቱ ሁሉ አድኖታል — ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ ሂፊል የተጠናቀቀ
2. ለቡድኑ
   ሀ. ያህዌ አድምጧል፣ ቁ. 6
   ለ. ያህዌ የተቸገሩትን አድኗል
   ሐ. የያህዌ መላእክት በሚፈሩት ዙሪያ ይሰፍራል (ዘካ. 9፡8፤ ያህዌ ራሱ መዝ. 125፡2 ላይ)
   መ. ያህዌ አድኗቸዋል
3. LXX፣ ሶርይኛ፣ ቫልጌት ቅጅዎች “መመልከት” እና “ማብራት” የሚል አላቸው፣ እንደ ተተኳሪ። ኤምቲ የተጠናቀቁ አሉት፣ 34፡5 ላይ።

*ታማኝ ተከታዮች ፈጽሞ ብቻቸውን ወይም የተተዉ አይሆኑም። የእነርሱ ታማኝ አምላክ ዘወትር ይኖራል፣ በዝግጁነት!*

**34፡7** “የእግዚአብሔር መልአክ” መላእክት የተዋጁት አገልጋዮች ናቸው (ዘኁ. 20፡16፤ መዝ. 91፡11፤ ኢሳ. 63፡9፤ ዳንε. 3፡28፤ 6፡22፤ ማቴ. 18፡10፤ ሐዋ. 12፡11፤ ዕብ. 1፡14)። ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

### ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር መልአክ

መለኮት ራሱን በሰው አካል መልክ በብሉይ ኪዳን መግለጡ የተለመደ ነው። ለሥላሴያውያን ጥያቄ የሚሆነው የትኛው የሥላሴ አካል ይሄንን ሚና እንደሚጫወት ነው። እግዚአብሔር አብ (ያህዌ) እና የእሱ መንፈስ በቋሚነት ሥጋዊ እንዳለመሆናቸው፣ ማለት የሚቻል የሚመስለው እነዚህ የሰው መገለጦች የቅድመ-ሥጋዊ መሲሕ ናቸው።

ማንም ሊገጥመው የሚችለውን ችግሮች ለማሳየት፣ ከመላእክት መከሰት ጋር ያለውን ትርጉም ለመለየት የሚከተለው ዝርዝር ገላጭ ነው፡

1. የእግዚአብሔር መልአክ እንደ መልአክ
   ሀ. ዘፍ. 24፡7፤40
   ለ. ዘጸ. 23፡20-23፤ 32፡34
   ሐ. ዘኁ. 22፡22
   መ. መሳ. 5፡23
   ሠ. II ሳሙ. 24፡16
   ረ. I ዜና. 21፡15-30
   ሰ. ዘካ. 1፡12-13
2. የእግዚአብሔር መልአክ እንደ መለኮት (ቲኦፋኒ)
   ሀ. ዘፍ. 16፡7-13፤ 18፡1-19፡1፤ 22፡11-15፤ 31፡11፤13፤ 48፡15-16
   ለ. ዘጸ. 3፡2፤4፤ 14፡19 (13፡21)

ሐ. መሳ. 2:15፤ 6:22-24፤ 13:3-23
መ. ሆሴዕ 12:3-4
ሠ. ዘካ. 3:1-5

▣ **"በሚፈሩት"** ይህ ቃል የድርጊት አንቀጽ ነው (ቢዲቢ. 431፣ ኬቢ. 432) እሱም ታማኝ ተከታዮችን የሚገልጽ (መዝ. 15:4፤ 25:12፣ 14፤ 31:19፤ 61:5፤ 66:16፤ 103:11፤ 118:4፤ ዘዳ. 28:58፤ ነሀ. 1:11)።

***መዝሙር ፡ 34፡8-14***

**8እግዚአብሔር ቸር እንደ ሆነ ቅመሱ እዩም**
**በእርሱ የሚታመን ሰው ምስጉን ነው።**
**9የሚፈሩት አንዳችን አያጡምና**
**ቅዱሳኑ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ፍሩት።**
**10ባለጠጎች ደኸዩ፥ ተራቡም፥**
**እግዚአብሔርን የሚፈልጉትን ግን ከመልካም ነገር ሁሉ አይጐድሉም።**
**11ልጆቼ ኑ፥ ስሙኝ**
**እግዚአብሔርን መፍራት አስተምራችኋለሁ።**
**12ሕይወትን የሚፈቅድ ሰው ማን ነው?**
**በጎንም ዘመን ለማየት የሚወድድ?**
**13አንደበትህን ከክፉ ከልክል፥**
**ከንፈሮችህም ሽንገላን እንዳይናገሩ።**
**14ከክፉ ሽሽ መልካምንም አድርግ**
**ሰላምን እሻ ተከተላትም።**

**34፡8-14** ያህዌ "መልካም" በመሆኑ (ቢዲቢ. 373 II)፣ የእርሱ ታማኝ ተከታዮች (ማለትም፣ ቅዱሳን፣ ቢዲቢ. 872) ማሳሰቢያ ተደርጎላቸዋል

1. ለመቅመስ — ቢዲቢ. 380፣ ኬቢ. 377፣ ቃል ተተኳሪ፣ ዕብ. 6:5
2. ለማየት – ቢዲቢ. 406፣ ኬቢ. 1157፣ ቃል ተተኳሪ፣ (በጴጥሮስ የተጠቀሰ 1 ጴጥ. 2:3 ላይ ከLXX)
3. ለመታመን – ቢዲቢ. 340፣ ኬቢ. 337፣ ቃል ተተኳሪ፣
4. ለመፍራት – ቢዲቢ. 431፣ ኬቢ. 432፣ ቃል ተተኳሪ፣

5፣6. ለመምጣት (ቢዲቢ. 229፣ ኬቢ. 246፣ ቃል ተተኳሪ)፣ ማድመጥ (ቢዲቢ. 1033፣ ኬቢ. 1570፣ ቃል ተተኳሪ) መዝሙረኛው እግዚአብሔርን መፍራት እንዲያስተምር፣ ቁ. 11

የእነርሱ ድርጊቶች ውጤቶቻቸው

1. የሚያጡት አይኖርም፣ ቁ. 9ለ፤ መዝ. 23፡1
2. ከመልካም ነገር የሚጎድላቸው አይኖርም፣ ቁ. 10ለ፤ መዝ. 84፡11
3. ረጅም ዕድሜ፣ ቁ. 12

የመዝሙረኛው ትምህርት ለረጅም፣ ደስተኛ ሕይወት እነሆ።

1. አንደበትህን ክፉ ከመናገር ከልክል፣ ከንፈርህንም ሽንገላን እንዳይናገሩ – ቢዲቢ. 665፣ ኬቢ. 718፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 12:3-4፤ 15:2-3፤ 73:8-9፤ ያዕቆብ 3:5-12
2. ከክፉ ራቅ – ቢዲቢ. 693፣ ኬቢ. 747፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 37:27፤ ኢሳ. 1:16
3. መልካምን አድርግ – ቢዲቢ. 793፣ ኬቢ. 889፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 37:27፤ ኢሳ. 1:17
4. ሰላምን እሻ – ቢዲቢ. 134፣ ኬቢ. 152፣ ፒይል ተተኳሪ፣ ማርቆስ 9:50፤ ሮሜ. 14:19፤ 1 ቆሮ. 7:15፤ 2 ቆሮ. 13:11፤ 1 ተሰ. 5:13፤ ዕብ. 12:14፤ ያዕቆብ3:17-18
5. ሰላምን ተከተል – ቢዲቢ. 922፣ ኬቢ. 1191፣ ቃል ተተኳሪ፣ እንደ ቁ. 4

ሚዛኑን አስተውል፣ ያህዌ ለታማኝ አገልጋዮች ባደረገው እና እነርሱ ለራሳቸው ማድረግ ባለባቸው መካከል ያለውን። ምርጫዎችና ውጤቶች ይኖራሉ፣ ሁለቱም አዎንታዊም ሆነ አሉታዊ (ቀጣዩ አንጓ ከፊል ዝርዝር ነው)!

ጴጥሮስ ከዚህ መዝሙር ላይ ጠቅሷል፣ 1 ጴጥሮስ 3 ላይ።

1. 1 ጴጥ. 3:10 – መዝ. 34:12፣13
2. 1 ጴጥ. 3:11 – መዝ. 34:14
3. 1 ጴጥ. 3:12 – መዝ. 34:15-16

እሱም የተመለከተው በእርሱ የአንድነት ኅብረት አጽንዖት አኳያ ነው (ማለትም፣ "ሁላችሁ በአንድ ልብ ሁኑ፣ የሌላው መከራ ለእናንተ እንደሚሆን አድርጉ፣ እንደ ወንድሞች ተዋደዱ፣ ርኅሩኆችና ትሑታን ሁኑ፣ ክፉን በክፉ ፈንታ ወይም ስድብን በስድብ ፈንታ አትመልሱ፣ ባርኩ እንጂ፣" 1 ጴጥ. 3፡8-9)።

**34፡8 "ጌታ መልካም ነው"** "መልካም" (ቢ.ዲ.ቢ. 373 II) በዚህ አንጓ ላይ ቁልፍ ቃል ነው (1 ተሰ. 5፡15)።

1. ያህዌ መልካም ነው (ቅጽል)፣ ቁ. 8፣ መዝ. 25:8፤ 86:5፤ 100:5፤ 106:1፤ 107:1፤ 118:1፣29፤ 145:9፤ 1 ዜና. 16:34፤ ዕዝራ 3:11፤ ኤር. 33:11፤ ነህ. 1:7
2. በእርሱ የሚያምኑ ከመልካም ነገር አይጎድሉም (ቢ.ዲ.ቢ. 481 አወቃቀር ቢ.ዲ.ቢ. 375)፣ ቁ. 10፣ መዝ. 84፡11
3. እግዚአብሔርን መፍራት ረጅምና መልካም ዕድሜን ያመጣል (ቢ.ዲ.ቢ. 373) ቁ. 12
4. ከክፉ ራቅ መልካምን አድርግ (ቢ.ዲ.ቢ. 373)፣ ቁ. 14
5. የ "መልካም"ን አጠቃቀም ሮሜ 8፡28 ላይ ተገንዘብ

**34:9**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ቅዱሳን"** |
| **አየተመት፣ አኢመቅ** | **"ቅዱሳን"** |
| **አእቅ** | **"ሕዝብ"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"የተሰጡት"** |
| **የተእመቅ** | **"ቅዱስ ሕዝብ"** |

ቅጽሉ (ቢ.ዲ.ቢ. 872) ሊጠቅስ የሚችለው

1. መሢሕን፣መዝ. 16:3 (እንደ ዳዊት የመዳረሻ ዘር)
2. የሰማያዊው ጉባኤ መላእክት፣ ኢዮብ 5:1፤ 15:15፤ መዝ. 89:5-6፣7፤ ዳን. 8:13፤ ዘካ. 14:5
3. ታማኝ ተከታዮች

ሀ. ካህናት – ዘኁ. 16:5፣7፤ መዝ. 106:16 (አሮን)

ለ. ሌዋውያን – 2 ዜና. 35:3

ሐ. ነቢያት – 2 ነገ. 4:9

መ. ናዝራውያን – ዘኁ. 6:5፣8

ሠ. እስራኤል – ዘጸ. 19:6፤ ሌዋ. 11:44፣45፤ 19:7፤ 20:7፣26፤ 21:6፤ ዘኁ. 15:40፤ ዘዳ. 7:6፤ 14:2፣21፤ 26:19፤ 28:9

እዚህ የሚያመለክተው ታማኝ ተከታዮችን ነው።

**34:10**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት፣ አየተመት፣ አኢመቅ** | **"አናብስት"** |
| **LXX፣ ፔሺታ** | **"ዓለት"** |
| **የተእመቅ** | **"መሳፍንት"** |
| **NEB** | **"የማያምኑ" (ከዓረብኛ ሥርወ-ቃል)** |

ኤምቲ "አናብስት" አለው። ጥያቄው "ምናባዊው ምስያ ማንን ያመለክታል?" የሚል ነው። እሱም በተሻለ የሚያቃርናቸው ይመስላል፣ ከ "ትሑታን፣" "መከራ ከሚቀበሉት" ጋር ወይም ከ "ደሀ" ጋር (ቢ.ዲ.ቢ. 776) የቁጥር 2 እና 6።

**34:11 "ልጆች"** ይህ በጥሬው "ወንዶች ልጆች" ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 119)። በጥበብ ሥነ-ጽሑፍ መምህር "አባት" ይባላል፣ ተማሪዎችም "ወንዶች ልጆች" (ማለትም፣ ምሳ. 1:8፤ 4:1፣10፣20፤ 6:1፣20፤ 24:13፣21)።

**መዝሙር ፡ 34፡15-18**

**15የእግዚአብሔር ዓይኖች ወደ ጻድቃን**
**ጆሮቹም ወደ ጩኸታቸው ናቸውና።**
**16መታሰቢያቸውን ከምድር ያጠፋ ዘንድ**
**የእግዚአብሔር ፊት ክፉን በሚያደርጉ ላይ ነው።**
**17ጻድቃን ጮኹ፥ እግዚአብሔርም ሰማቸው**
**ከመከራቸውም ሁሉ አዳናቸው።**
**18እግዚአብሔር ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፥**
**መንፈሳቸው የተሰበረውንም ያድናቸዋል።**

**34፡15-18** ይህ አንጓ የሚያሳየው የመልካም ወይም መልካም ያልሆነ አኗኗርን ውጤት ነው።

1. ጻድቃን

ሀ. የያህዌ ዓይኖች (መገኘቱና ክብካቤው) ወደ ጻድቃን ናቸው፣ ቁ. 15ሀ

ለ. የያህዌ ጆሮዎች ጩኸታቸውን ያደምጣል፣ ቁ. 15ለ፣ 17

ሐ. ያህዌ ከችግራቸው ሁሉ ያድናቸዋል፣ ቁ. 17ለ

መ. ያህዌ ልባቸው ለተሰበረ ቅርብ ነው፣ ቁ. 18ሀ

ሠ. ያህዌ መንፈሳቸው የተሰበረውን ያድናቸዋል፣ ቁ. 18ለ፤ ኢሳ. 57፡15

2. ኃጥአን
   ሀ. የያህዌ ፊት ክፉን በሚያደርጉ ላይ ነው፣ ቁ. 16ሀ
   ለ. መታሰቢያቸው ይቆረጣል (ቢዲቢ 503፣ ኬቢ 500፣ ሂፊል ያልተወሰነ አወቃቀር)፣ ቁ. 16ለ፤ ይህ ምስያ ሞትን ያመለክታል

በርካታ ሰውኛ ዘይቤዎች በዚህ አንጓ ላይ ይገኛሉ፣ የሰውን አካል የሚጠቀሙ ያህዌን ለመግለጽ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 2፡4-6 ላይ)።

1. ዓይን
2. ጆሮ
3. ፊት

**34፡18 "ጌታ ቅርብ ነው"** እንዴት ያለው አስደናቂ ተስፋ ነው (ዘዳ. 4:7፤ መዝ. 119:51፤ 145:18)። አስደንጋጭ የሚሆነው ቅዱስ አምላክ ከኃጢአተኛ ሰዎች ጋር ኅብረት ለማድረግ መፈለጉ ነው። እሱ ይፈልገናል ይከተለናልም። የተፈጠርነው በእርሱ ነው ከእርሱ ጋር ለሆነ ኅብረት (ዘፍ. 1:26፣27፤ 3:8)። ምንም ዓይነት መጥፎ ነገር ቢያገኛቸው (ማለትም፣ "ልባቸው የተሰበረ፣" መዝ. 147:3፤ ኢሳ. 61:1 እና "መንፈሳቸው የተሰበረ፣" መዝ. 51:17፤ ኢሳ. 57:15)፣ ጌታ ለታማኝ ተከታዮች ቅርብ ነው!

**መዝሙር ፡ 34፡19- 22**

**[19]የጻድቃን መከራቸው ብዙ ነው፥**
**እግዚአብሔርም ከሁሉ ያድናቸዋል።**
**[20]እግዚአብሔር አጥንቶቻቸውን ሁሉ ይጠብቃል፥**
**ከእነርሱም አንድ አይሰበርም።**
**[21]ኃጢአተኞችን ክፋት ይገድላቸዋል**
**ጻድቃንንም የሚጠሉ ይጸጸታሉ።**
**[22]የባሪያዎቹን ነፍስ እግዚአብሔር ይቤዣል፥**
**በእርሱም የሚያምኑ ሁሉ አይጸጸቱም።**

**34፡19-22** ይህ አንጓ የሚቀጥለው የፊተኛውን አጽንዖት ነው፣ ነገር ግን አጽንዖት የሚሰጠው የተለያዩ ውጤቶችን ነው፣ በመልካምና መልካም ባልሆነ መካከል። የመጨረሻዎቹ ሁለቱ አንጓዎች የሁለተኛ ደረጃ ትይዩዎች ናቸው።

1. የያህዌ ድርጊት፣ በታማኝ ተከታዮቹ አኳያ
   ሀ. እሱም ከበርካታ ችግራቸው ሁሉ ያድናቸዋል፣ ቁ. 19
   ለ. እሱም አጥንታቸው ሁሉ እንዳይሰበር ይጠብቃል፣ (ማለትም፣ የጤንነት ምስያ)፣ ቁ. 20
   ሐ. እሱም ይዋጃል (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 19፡14 ላይ) ባሪያዎቹን፣ ቁ. 22ሀ
   መ. በእርሱ የሚታመኑ ሁሉ አይጸጸቱም፣ ቁ. 22ለ
2. የያህዌ ድርጊቶች ታማኝ ባልሆኑት ላይ
   ሀ. ኃጢአተኞችን ይገድላቸዋል፣ ቁ. 21ሀ (ዝከ. ቁ. 16)
   ለ. ጻድቃንን የሚጠሉ ሁሉ ይጸጸታሉ፣ ቁ. 21ለ

**34፡19** ስለዚህ ቁጥር ሁለት ነጥቦች ይኖራሉ።

1. ጻድቅ በዚህ በወደቀ ዓለም መከራን ተቀብሏል/እየተቀበለም ነው/ይቀበላልም (መዝ. 37:39፤ 50:15፤ ዳን. 12:1፤ Matt. 5:10-12፤ ዮሐንስ 15:18-21፤ 16:1-3፤ 17:14፤ Acts 14:22፤ ሮሜ. 5:3-4፤ 8:17፣18-23፤ 2 ቆሮ. 4:16-18፤ 6:3-10፤ 11:23-30፤ ፊሊ. 1:29፤ 1 ተሰ. 3:3፤ 2 ጢሞ. 3:12፤ ያዕቆብ 1:2-4፤ 1 ጴጥ. 4:12-16)።
2. እግዚአብሔር ከእነርሱ ጋር ነው፣ በእነዚህ መከራዎች ውስጥ። አንዳንድ ጊዜ በተአምራት ማዳንን ይመርጣል፣ ነገር ግን ዘወትር አያደርግም (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ.30፡2 ላይ)። የእርሱ መገኘት ታላቁ መሻታችንና ተስፋችን ነው። በምን ውስጥ እንደምናልፍ ያውቃል (ዘጸ. 3፡7)።

**34፡20** የሰው አጥንት መስበር ለእግዚአብሔር ፍርድ ፈሊጥ ነው (መዝ. 51:8፤ ኢሳ. 38:13፤ ሰቆ. 3:4)። ስለዚህ፣ ምንም አጥንት አለመሰበሩ ምንም ፍርድ እንደማይገባው ማሳያ ፈሊጥ ነው (ማለትም፣ ጻድቅ ሰው)።

ይህ ቁጥር የተጠቀሰው በዮሐንስ ወንጌል ላይ ነው (ዮሐንስ 19፡36፣ ከዘካ. 12፡10 ጋር ተጎዳኝቶ፣ ዮሐንስ 19፡37 ላይ) እንደ ትንቢታዊ ትንበያ። እኔ እንደማስበው እንደ ዋነኛ ምድባዊ መረዳት መውሰዱ ይመረጣል። መዝሙር 34፡20 ስለ መሢሕ ሞት ትንበያ አይደለም ነገር ግን ስለ ታማኝ ተከታይ ጤንነትና ደኅንነት የተሰጠ ተስፋ እንጂ።

እዚህጋ ያለው ችግር፣ ሥነ-ትርጓሜያዊው ንድፈ-ሐሳብ የሚያስረግጠው የተመስጧዊው ደራሲ ዋነኛው ሐሳብ ጽሑፉን እንዴት መረዳት እንደሚቻል የመጀመሪያው ስፍራ ጽሑፋዊ እና ታሪካዊ ዐውድ መሆኑ ነው። ይህ በርግጥ እውነት ነው። ነገር ግን የአኪ ተመስጧዊ ደራስያን ዋነኛውን ምድብ በተገቢው እንደሚጠቀሙበት መፍቀድ ይኖርብናል። እኛ የእነርሱን ዘዴ ዳግም መፍጠር

አንችልም፣ ምክንያቱም ተመስጧዊ ስላልሆንን፣ እነርሱ ግን ነበሩ። ስለዚህ፣ በእነዚህ ምክንያቶች የአኪ አጠቃቀም ዋጋ ሊኖረው ይገባል፣ ነገር ግን ዘወትር የሚሆነው ለብኪ ደራሲ መደነቂያ ነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወስን አይደለም።

1. "የእግዚአብሔር መልአክ" ማን ነው? መዝሙራት ላይ ሌላ የት ስፍራ ነው የተጠቀሰው?
2. ቁጥር 8 በአኪ እንዴትና ለምን ሁለት ጊዜ ተጠቀሰ (ዕብ. 6:5፤ 1 ጴጥ. 2:3)?
3. ደራሲው አድማጮቹን ለምን "ልጆቼ" ብሎ ጠራቸው?
4. የሰውን አካል ክፍሎች ዘርዝር፣ ያህዌን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን፣ ቁጥር 15-17 ላይ።
5. "አጥንቶቹን ሁሉ ይጠብቃል" የሚለው የዕብራይስጥ ፈሊጥ ምን ማለት ነው?
6. የቁጥር 19 አንድምታዎች ምንድናቸው፣ በወደቀው ዓለም?
7. "ነፍስ" የሚለው ቃል በብኪ ምን ማለት ነው?

# መዝሙር 35
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ከጠላቶች ስለመታደግ ጸሎት <u>ኤምቲ መግቢያ</u> "የዳዊት መዝሙር።" | ጌታ የሕዝቡ ተበቃይ | ከግል ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት (ሰቆቃ) | የዕርዳታ ጸሎት | የንጹሕ ጸሎት በመከራ ጊዜ |
| 35:1-8 | | | | 35:1-3 |
| | 35:1-3 | 35:1-3 | 35:1-3 | |
| | | | | 35:4 |
| | 35:4-8 | 35:4-6 | 35:4-6 | |
| | | | | 35:5-6 |
| | | | | 35:7-8 |
| | | 35:7-8 | 35:7-8 | |
| 35:9-16 | | | | 35:9-10 |
| | 35:9-10 | 35:9-10 | 35:9-10 | |
| | | | | 35:11-12 |
| | 35:11-14 | 35:11-12 | 35:11-14 | |
| | | | | 35:13-14 |
| | | 35:13-14 | | |
| | | | | 35:15-16 |
| | 35:15-16 | 35:15-16 | 35:15-16 | |
| 35:17-21 | | | | 35:17-18 |
| | 35:17-18 | 35:17-18 | 35:17-18 | |
| | | | | 35:19 |
| | 35:19-21 | 35:19-21 | 35:19 | |
| | | | | 35:20-21 |
| | | | 35:20-25 | |
| 35:22-26 | | | | 35:22-24 |
| | 35:22-25 | 35:22-25 | | |
| | | | | 35:25-26 |
| | 35:26 | 35:26 | 35:26 | |
| 35:27-28 | | | | 35:27 |
| | 35:27-28 | 35:27-28 | 35:27-28 | |
| | | | | 35:28 |

## የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

5. የመጀመሪያው አንቀጽ
6. ሁለተኛው አንቀጽ
7. ሦስተኛ አንቀጽ
8. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር በብዛት ያለው
  4. የጸሎት ጥያቄዎች (8 ተተኳሪዎች) ለያህዌ ዕዳታ፣ በጠላቶች ላይ
  5. ተጽዕኗዊ (23) መዝሙረኛው እንዲሆኑ ተስፋ የሚያደርጋቸው
    ሀ. በጠላቶቹ ላይ
    ለ. በደጋፊዎቹ ላይ

ለ. በአብዛኞቹ መዝሙራት ላይ ጠላቶቹ እነማን እንደሆኑ መለየት ያስቸግራል። እዚህ መዝሙር ላይ (ማለትም፣ 35፡12-14) እነርሱ የቅርብ የኪዳን ታዋቂ ሰዎች መሆናቸው ግልጽ ነው። ይህም የክህደቱን ሥቃይ እጅግ መራራ ያደርገዋል! ሆኖም፣ ቁጥር 1-8 የሚያመለክተው ወታደራዊ ባላንጣን ይምስላል።

ሐ. መዝሙር 34 እና መዝሙር 35 ብቸኛ መዝሙራት ናቸው፣ "የእግዚአብሔር መልአክ" የተጠቀሰባቸው። ይህም ተከታትለው ለመቀመጣቸው ምክንያት ሊሆን ይችላል። መዝሙሮቹ ተመርጠው፣ ታርመው፣ እና ተጠናቅረው ተቀምጠዋል፣ ባልታወቁ ሰዎችና ባልታወቀ ሂደት። በእምነት እናምናለን፣ በመንፈስ እንደተመሩ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 35፥1-8**

**[1]አቤቱ፥ የሚበድሉኝን በድላቸው፥**
**የሚዋጉኝንም ተዋጋቸው።**
**[2]ጥሩርና ጋሻ ያዝ፥**
**እኔንም ለመርዳት ተነሥ።**
**[3]ሰይፍህን ምዘዝ የሚያሳድዱኝንም መንገዳቸውን ዝጋ**
**ነፍሴን፦ መድኃኒትሽ እኔ ነኝ በላት።**
**[4]ነፍሴን የሚሹ ሁሉ ይፈሩ ይጐስቈሉም**
**ክፉትን በእኔ ላይ የሚያስቡ ይፈሩ ወደ ኋላቸውም ይበሉ።**
**[5]በነፋስ ፊት እንዳለ ትቢያ ይሁኑ፥**
**የእግዚአብሔርንም መልአክ ያስጨንቃቸው።**
**[6]መንገዳቸው ዳጥና ጨለማ ይሁን፥**
**የእግዚአብሔርም መልአክ ያሳድዳቸው።**
**[7]በከንቱ ያጠፉኝ ዘንድ ወጥመዳቸውን ሸሽገውብኛልና፥**
**ነፍሴን በከንቱ አበሳጭተዋልና።**
**[8]ያላወቁት ወጥመድ ይምጣባቸው፥**
**የሸሸጉትም ወጥመድ ይያዛቸው**
**በዚህ ወጥመድ ውስጥ ይውደቁ።**

**35፥1-8** ይህ አንጓ የሚጀምረው በበርካታ የጸሎት ጥያቄዎች ነው (ተተኳሪዎች) ቁጥር 1-3።

1. በድላቸው – ቢዲቢ 936፣ ኬቢ 1224፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ ስሙ የሚከሰተው ሁለተኛው ሐረግ ላይ ነው (ቢዲቢ 937)
2. ተዋጋቸው – ቢዲቢ 535፣ ኬቢ 526፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ *ቃል* አንቀጽ የሚከሰተው ሁለተኛው ሐረግ ላይ ነው
3. ያዝ – ቢዲቢ 304፣ ኬቢ 302፣ *ሂፊል ተተኳሪ* ("ኃይል ያዝ")
4. ተነሥ – ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ *ቃል ተተኳሪ*
5. ምዘዝ – ቢዲቢ 937፣ ኬቢ 1227፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ ዘጸ. 15፡9
6. ኤምቲ "ቅረብ" የሚል አለው – ቢዲቢ 688፣ ኬቢ 742፣ *ቃል ተተኳሪ* (አኪጀት፣ LXX፣ አዓት) ግን ተመሳሳይ ተናባቢዎች የሚሉት "የውጊያ ፍላጻ" ነው (ሔሮዶቱስ፣ አአመመቅ፣ አየተመት፣ አኢመቅ፣ ጄፒኤስኦኤ)። የዩቢኤስ ጽሑፍ ፕሮጀክት ለተተኳሪው "ሀ" ደረጃ ይሰጠዋል። የዕብራይስጡ ተናባቢዎች "የጦርነት ፍላጻ፣" "ጦር፣" "አንካሴ" በሚል ሊተረጎሙ ይችላሉ፤ እሱም በብኪ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው። አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ መዝሙረኛው ጠላቶቹ የሚላቸው እነማን እንደሆኑ የሚጠቅሰውን።
   1. ወታደራዊ ተዋጊዎች፣ ቁ. 1-3፣ 4-6
   2. ሕጋዊ ጠላቶች፣ ቁ. 11
   3. የቅርብ ወዳጆች፣ ቁ. 12-14
7. በል – ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል ተተኳሪ*። ይህ ሐረግ የቁን ያህል ግለሰባዊ እንደሆነ ተገንዘብ። መዝሙረኛው ያህዌን ፈልጓል፣ እሱ ብቸኛው ታዳጊው እንደሆነ እንዲያረጋግጥለት፣ መዝ. 62፡2፤ 89፡26። ደኅንነት/ትድጊያ የሚኖር ከሆነ የሚመጣው ከኪዳን አምላክ፣ ከያህዌ ነው!

▣ ከመዝ. 35፡4-8 ጀምሮ መዝሙረኛው ያህዌን ይጠይቃል

1. እነርሱ ይፈሩ – ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 4፤ መዝ. 40፡14፤ 70፡2፤ 83፡17
2. ክብራቸውን ይጡ – ቢዲቢ 483፣ ኬቢ 480፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 4
3. ወደ ኋላቸው ይመለሱ – ቢዲቢ 690፣ ኬቢ 744፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ቁ. 4
4. ይዋረዱ – ቢዲቢ 344፣ ኬቢ 340፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ.4
5. በነፋስ ፊት እንዳለ ገለባ ይሁኑ – ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 5፤ ኢዮብ 21፡18፤ መዝ. 1፡4
6. መንገዳቸው ዳጥና ጨለማ ይሁን – ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ *ቃል* ተጽዕኗዊ ቁ. 6
7. ያላወቀው ጥፋት ይምጣበት – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 8
8. የሸሸገው ወጥመድ ይያዘው – ቢዲቢ 539፣ ኬቢ 530፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 8 (ሁነኛ የመጽሐፍ ቅዱስ ምሳሌያዊ የተገላቢጦሽ፤ መዝ. 9፡15፤ 31፡4፤ 140፡5፤ 142፡3)
9. በገዛ ራሱ ክፉ ሐሳብ ላይ ይውደቅ – ቢዲቢ 656፣ ኬቢ 709፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 8

▣ እነዚህ ጠላቶች ባሕርያቸው

1. ነፍሴን የሚሹ – ቢዲቢ 134፣ ኬቢ 153፣ *ፒዬል* አንቀጽ፣ ቁ. 4

2. በእኔ ላይ ክፉ የሚያስቡ – ቢዲቢ 362፣ ኬቢ 359፣ *ቃል* አንቀጽ፣ ቁ. 4
3. በእኔ ላይ በከንቱ ወጥመድ ሸሽገውብኛልና – ቢዲቢ 380፣ ኬቢ 377፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ቁ. 7
4. በከንቱ ነፍሴን ያጠፉ ዘንድ ጉድጓድ ቆፍረውብኛልና – ቢዲቢ 343፣ ኬቢ 340፣ *ቃል* የተጠናቀቀ ቁ. 7 (ይህ ለአጽንዖት እንደተደገመ ተገንዘብ)

**35:2 "ጥሩርና ጋሻ"** እነዚህ (ቢዲቢ 857፣ ኬቢ 1037 እንደ ቢዲቢ 171፣ ኬቢ 545) የጋሻ ዓይነቶች ናቸው። ቢዲቢ "ጥሩር"ን የሚገልጸው (ቢዲቢ 857) ተለቅ ያለ፣ ሙሉ አካልን እንደሚሸፍን ጋሻ ሲሆን፣ የሌለኛውን መጠን አይሰጥም። ሊሆን የሚችለውም፣ ሁለቱም በጦርነት ጊዜ በወታደሮች መያዛቸውን ነው (እና/ወይም የጦር መሣርያ ያዣቸው)። ስለዚህ፣ አንደኛው ለጦርና ለቀስት ሲሆን (ሙሉ አካል) አንደኛውም የእጅ ለእጅ ግጥሚያ ነው (አነስ ያለው፣ ቢዲቢ 171፤ ኒዶቲ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 846)።

**35:3 "የሚያሳድዱኝ"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 922፣ ኬቢ 1191፣ *ቃል* የድርጊት አንቀጽ) ዘወትር በመዝሙራት ጥቅም ላይ ይውላል፣ ለግፈኛ ጠላቶች (መዝ. 7:1፣5፤ 31:15፤ 71:11፤ 109:16፤ 119:84፣86)። ሊሆን የሚችለውም

1. ወታደራዊ ማሳደድ
2. የአደን ማሳደድ
3. ለግፈኛ ጠላት ዘይቤ

**35:5-6 "የእግዚአብሔር መልአክ"** መላእክት የሚከላከሉ አካላት ናቸው፣ መዝ. 34:7 ላይ፣ ነገር ግን እዚህ የፍርድ አካላት ናቸው። አንዳንዶች ይላሉ፣ መጽሐፍ ቅዱስ፣ ጥንታዊ ቅድመ-ሳይንሳዊ መጽሐፍ ስለሆነ፣ ስለማይታየው፣ ስለማይገለጸው አፈታሪካዊ ነው። እሱም በርግጠኝነት እውነት ነው፣ እዚህጋ ምሥጢር ለመኖሩ፣ ነገር ግን አንዱ መጽሐፍ ቅዱስን የእውነተኛው አንዱ አምላክ የተለየ መገለጥ መሆኑን ከተቀበለ፣ ከዚያም እሱ/እሷ የእርሱን ርዕዮተ-ዓለም መቀበል ይኖርባቸዋል፣ ይኸውም በሚታየውና በማይታየው ዓለም መካከል ያለውን ግንኙነትንም የሚያካትት። በርግጠኝነት እንዴት፣ መቼ፣ የት፣ ማን በዚህ ግንኙነት ላይ እንደሚያያዝ አልተረጋገጠም።

እሱም ለማወቅ ዘወትር አስቸጋሪ ነው፣ በመካከላቸው ያለውን ልዩነት፣ በጽሑፋዊ አጠቃቀም (ለመልእክት ጥቅም ላይ የዋለ) እና ጥሬያዊ አጠቃቀም (ማለትም፣ የመላእክት ጣልቃ ገብነት ወይም ድርጊት)። እዚህጋ ሁለት ድግግሞሾች አሉ— እያንዳንዱ ነገር መልአካዊ ተጓዳኝ አለው አልያም ምንም ነገር መልአካዊ ተጓዳኝ የለውም። የምንኖረው በእምነትና በመጽሐፍ ቅዱሳዊ መገለጥ ነው። አካላትን መለየት የሚገባው በአንድ በኩል ወይም በሌላው ነው።

ሕይወት ዘወትር "ጨለማ" እና "ዳጥማ" ነው (መዝ. 73:18) ያህዌን ለሚታመኑት ግን እሱ በሸለቆ(ዎች) በድቅድቅ ጨለማ አብሯቸው ይጓዛል (መዝ. 23:4፤ 107:14)። ሕይወት ዘወትር የሚገለጸው በዘይቤአዊ ቋንቋ ነው፣ በ'ርምጃ ወይም በጉዞ። ቀጥተኛ፣ የተስተካከለ፣ የተደለደለ መንገድ ለመልካም ሕይወት ምስያ ሲሆን፣ ጨለማ፣ ዳጥ፣ መሰናከል በመንገድ ላይ ሲሆን ወይም ያልተስተካከለ መንገድ የችግር ተምሳሌት ነው።

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር መልአክ፣ መዝ. 34:7 ላይ።

## መዝሙር ፡ 35:9-16

**9 ነፍሴ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይላታል፥**
**በማዳኑም ሐሴት ታደርጋለች።**
**10 አጥንቶቼ ሁሉ እንዲህ ይሉሃል። አቤቱ፥ እንደ አንተ ማን ነው?**
**ችግረኛን ከሚቀማው እጅ፥**
**ችግረኛንና ድሀውንም ከሚነጥቀው እጅ ታድነዋለህ።**
**11 የከፉት ምስክሮች ተነሡብኝ፥**
**የማላውቀውንም በእኔ ላይ ተናገሩ።**
**12 ስለ በጎ ክፋትን መለሱልኝ፥**
**ነፍሴንም ልጆችን አሳጡአት።**
**13 እኔስ እነርሱ በታመሙ ጊዜ ማቅ ለበስሁ፥**
**ነፍሴንም በጾም አደከምኋት**
**ጸሎቴም ወደ ብብቴ ተመለሰ።**
**14 ለወዳጄና ለወንድሜ እንደማደርግ አደረግሁ ለ**
**እናቱም እንደሚያለቅስ ራሴን ዝቅ ዝቅ አደረግሁ።**
**15 በእኔ ላይ ተሰበሰቡ ደስም አላቸው**
**ግፈኞች በእኔ ላይ ተሰበሰቡ**
**እኔም አላውቅሁም ቀደዱኝ አልተውኝምም።**
**16 ፈተኑኝ በሣቅም ዘበቱብኝ፥**
**ጥርሳቸውንም በእኔ ላይ አንቀጫቀጩ።**

**35:9-16** ይህ አንጓ የያህዌን ማዳን ያረጋግጣል።

1. ነፍሴ በእግዚአብሔር ደስ ይላታል – ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
2. በማዳኑም ሐሴት ታደርጋለች – ቢዲቢ 965፣ ኬቢ 1314፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
3. አጥንቶቼ ሁሉ (ማለትም፣ ነፍሱ፣ መዝ. 51:8) ይላሉ – ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ (ማለትም፣ "ነፍስ" *ኔፊሽ* [ቢዲቢ 659]፣ እና "አጥንቶች" ፈሊጦች ናቸው፣ ለሙሉ አካል፣ መዝ. 6:2)
ሀ. እንዳንተ ማን ነው፣ ዘጸ. 15:11፤ መዝ. 86:8፤ ሚኪያስ 7:18፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት፣ መዝ. 2:7 ላይ
ለ. ችግረኛውን የሚያድነው

በዚህ ነጥብ ላይ (35:11) መዝሙረኛው ጠላቶቹን መግለጽ ይጀምራል።

1. የክፋት ምስክሮች — ቢዷቢ 729 አወቃቀር ቢዷቢ 329፣ ቁ. 11
2. የማያውቀውን ነገር የሚጠይቁት፣ ቁ. 11 (መቼቱ የፍርድ ችሎት ነው፣ የሐሰት ምስክሮቹም መዝሙረኛው ስላላደረገው ነገር ይጠይቃሉ)
3. ስለ መልካም ፈንታ ክፉ የሚመልሱ፣ ቁ. 12፣ መዝ. 38:20፤ 109:5 (የተገላቢጦሽ፣ ዝከ. ቁ. 13-14)
4. በመሰናከሉ የሚደሰቱ፣ ቁ. 15
5. ሐሰትን ሊናገሩበት በእርሱ ላይ የሚሰበሰቡ፣ ቁ. 15
6. በእርሱ ላይ ጥርሳቸውን የሚያንቀጫቅጩ ቁ. 15፣ መዝ. 37:12፤ 112:10፤ ኢዮብ 16:9፤ ሰቆ. 2:16፤ ማቴ. 8:12፤ 25:30፤ ሉቃስ 13:28

መዝ. 35:14 እና 15 መዝሙረኛው ስለሚያሳድዱት ይገልጻል፣ ምን እንዳደረገላቸው

1. በታመሙ ጊዜ፣ እሱ ስለ እነርሱ ማቅ ለበሰ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የኀዘን ሥርዓት፣ መዝ. 30፡11 ላይ)
2. እሱ ራሱን ዝቅ አደረገ፣ ጾመ፣ ጸለየም፣ በእነርሱ አኳያ
3. ስለ እነርሱ አዘነ (እንደ ቅርብ ወዳጅ ወይም ወንድም)
4. ስለ እነርሱ አዘነ (ለገዛ እናቱ እንደሚያደርግ)

የሚታይ ተቃርኖ አለ፣ ታማኝ ተከታይ በሚያደርገው እና ያልታመነው በሚያደርገው መካከል! ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በግልጽ ይታያል፣ ሌሎችን በምንይዝበት አገባብ።

**35፡12ለ** ኤምቲ "የወዳጅ መለየት ኀዘን" የሚል አለው (ቢዷቢ 1013) ከልጆች ሞት የተነሣ፣ እሱም መራራ ኀዘን የሆነ። አእመቅ ማስተካከያ ያቀርባል፣ "ሕይወቴን ፈለጓት"፤ የተእመቅ፣ "ሕይወቴን ሊወስዱ አደቡ።"

አዘውትሮ እውነት እንደሆነው፣ ዘመናዊዎቹ አንባቢዎች የጥቅምን (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ቅኔ ሙሉ ለሙሉ ሊገነዘቡ አይችሉም። ሆኖም፣ ምንም እንኳ ያልፎ አልፎ ቃላት እና ርግጠኛ ያልሆነ ምናባዊ ምስያ ቢኖርም፣ አጠቃላይ ፍሬ ሐሳቡን ከዐውደ-ጽሑፉ፣ በተለይም ከትይዩነቱ መገንዘብ ይቻላል።

**35:13ለ**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ LXX** | **"ጸሎቴም ወደ ብብቴ ተመለሰ"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"የጸለይኩት ሆነብኝ"** |
| **አየተመት፣ አእቅ** | **"ራሴን ወደ ሆዴ አዘቅዝቄ ጸለይኩ"** |
| **አኢመቅ** | **"በልቤ እንዳዲስ ጸለይኩ"** |

ኤምቲ ርግጠኛ አይደለም። ስለዚህ ትርጉሞቹ የሚሉት

1. መዝሙረኛው ለጠላቶቹ የጸለየውና ያደረገው፣ 35፡13-14 ላይ ለራሱ ጥቅም ተቀየረ፣ ለእነርሱ ሳይሆን (ማቴ. 10፡13፤ ሉቃስ 10፡6)
2. ሐረጉ የሚያመለክተው በጸሎት ጊዜ የአካሉን አቀጣጫ ነው
3. ሐረጉ የሚያመለክተው የተደጋገመ ጸሎትን ነው

**35:15**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አየተመት፣ አኢመቅ፣ ጀፒኤስኦኤ፣ የተእመቅ** | **"ማሰናከያ"** |
| **አኪጀት፣ አእቅ** | **"ጠላትነት"** |
| **አእመቅ** | **"ባለጌ"** |

ኤምቲ "በእኔ መሰናከል" የሚል አለው (ቢዷቢ 854፣ መዝ. 38:17፤ ኢዮብ 18:12)። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ለኤምቲ "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል፣ (ሁነኛ ጥርጣሬ)። እሱም የሚያቀርበው ሐሳብ "የሚያነክስ ዓይነት" የሚል ነው፣ የተጎዳውን መዝሙረኛ ለማሳየት (ገጽ 220)። የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 335) የሚለው መዝሙረኛው እንደ ቆሰለ እንስሳ ያነክስ ነበር። እንደዚያ ከሆነ "አንድ ላይ መሰብሰብ" እንደ ውሻ መንጋ ዓይነት ነው።

**35:16**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በግብዣ ላይ እንደሚቀልዱ ባለጌዎች"** |
| **አኪጀት** | **"በግብዣ ላይ እንደሚያፌዙ ባለጌዎች"** |
| **አየተመት** | **"በባለጌ ፌዛቸው ቀጠሉበት"** |
| **አእቅ** | **"በሽባ ላይ እንደሚያፌዙ ዓይነት"** |
| **አኢመቅ** | **"ብወድቅ ከበቡኝ"** |
| **የተእመቅ** | **"ሲያዳልጠኝ አፌዙብኝ"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"በቀልድና ፌዝ ፊት ማጨማደድ"** |

ኤምቲ "እንደ ባለጌ ፌዘኞች" የሚል አለው፣ እሱም በግልጽ ስሜት የማይሰጥ የሆነ። ስለዚህ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ትይዩነትን ለማግኘት ይሞክራሉ፣ በቁጥር 15 እና በቁጥር 16 መካከል፣ ነገር ግን እሱ መስተዋድድ ብቻ ነው። ኤቢ (ገጽ 214) ማሻሻያ ያቀርባል፣ "በፌዘኞች መከበቤ" የሚል ስሜት ያለው።

ኤምቲ የመጀመሪያው ወይም የድሮው የዕብራይስጥ የእጅ ጽሑፍ አይደለም።

## መዝሙር ፡ 35፡17-21

**17 አቤቱ፥ እስከ መቼ ድረስ ታይልኛለህ?**
**ነፍሴን ከክፉ ሥራቸው**

**ብችነቴንም ከአንበሶች አድናት።**

**[18]አቤቱ፥ በታላቁ ጉባኤ ውስጥ እገዝልሃለሁ፥**
**በብዙ ሕዝብ መካከልም አመሰግንሃለሁ።**
**[19]በግፍ የሚጠሉኝ በላዬ ደስ አይበላቸው፥**
**በከንቱ የሚጣሉኝም በዓይናቸው አይጣቀሱብኝ።**
**[20]ለእኔስ ሰላምን ይናገሩኛልና፥**
**በቍጣም ሽንገላን ይመክራሉ።**
**[21]አፋቸውንም በእኔ ላይ አላቀቁ**
**እሰይ እሰይ፥ ዓይናችን አየው ይላሉ።**

**35፡17-21** ከፊተኛው አንጻ በተለየ መልኩ፣ ይሄኛው የሚጀምረው ያህዌን ለምን በማለት በመጠየቅ ነው፣ ከዚያም ለድርጊት ይጸልያል።

1. እስከመቼ ድረስ ዝም ትላለህ – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ* (ተመሳሳይ ሐሳብ እንደ መዝ. 13:1-2፤ 22:1-2፤ ዕን. 1:2-4፤ ያህዌህ ምላሽ አልሰጠም፣ መዝሙረኛው እንዲያደርግ እንደሚያስበው)
2. አድን (*"መልስ"*) ነፍሴን – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

ቁጥር 18 የሚገልጸው መዝሙረኛው ምን እንደሚያደርግ ነው፣ ያህዌ ሲያድነው።

1. በታላቅ ጉባኤ መሐል አመሰግንሀለሁ (የመቅደስ ስብስብ፣ መዝ. 22:25፤ 40:9፣10) – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ፣ በኀብራዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. በታላቅ ሕዝብ መሐል አመሰግንሃለሁ (ተመሳሳይ ትይዩ ከቁ. 1 ጋር) – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ
3. 248፣ ፔል ያልተጠናቀቀ በኀብራዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

ቁጥር 19 "እነርሱ ይሁኑ..." ወደሚለው ፈርጅ ይመለሳል፣ የቁ. 5-8።

1. ያለምክንያት ጠላቶች የሆኑኝ በእኔ ላይ እንዲደሰቱ አትተዋቸው – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀበተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ወይም በከንቱ የጠሉኝ ዓይናቸውን በክፋት ያጣቅሱብኝ ዘንድ – ቢዲቢ 902፣ ኬቢ 1147፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ምሳ. 6:12-14፤ 10:10

መዝ. 35:20-21 ምክንያቶቹን ያስቀምጣል፣ ያህዌህ በጠላቶቹ ላይ ለምን እንደሚነሣ።

1. ሰላምን አይናገሩም
2. የስድብ ቃልን ይናገራሉ
3. አፋቸውን አላቀቁብኝ
4. እነርሱን አሉ፣ "እሰይ፣ እሰይ፣ ዓይናችን አየው"

**35፡14** ኢየሱስ የዚህን ቁጥር ክፋይ ዮሐንስ 15:25 ላይ ጠቅሶታል፣ በዐቢይ ምድባዊ መልኩ እሱን እንደሚጠቅስ።

**35፡17 "አንበሶች"** መዝሙር 34፡10 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት።

**35፡20 "በምድራቸው በጸጥታ ያሉ"** ይህ ሐረግ የተለየ ነው። ከትይዩው አኳያ እሱ የሚያመለክት የሚመስለው ችግርን የማይፈጥሩ ሰዎችን ነው፣ ሰላምን ፈላጊዎችን።

## መዝሙር ፡ 35፡22-26

**[22]አቤቱ፥ አንተ አየኸው ዝም አትበል አቤቱ፥**
**ከእኔ አትራቅ።**
**[23]አምላኬ ጌታዬም፥ ወደ ፍርዴ ተነሥ፥**
**አቤቱ፥ ፍርዴን አድምጥ።**
**[24]አቤቱ አምላኬ፥ እንደ ጽድቅህ ፍረድልኝ፥**
**በላዬም ደስ አይበላቸው።**
**[25]በልባቸው። እሰይ እሰይ፥ ነፍሳችንን ደስ አላት አይበሉ**
**ደግሞም፦ ዋጥነው አይበሉ።**
**[26]በመከራዬ ደስ የሚላቸው ይፈሩ፥ በአንድነትም ይጐስቍሉ**
**በእኔ ላይ የሚታበዩ እፍረትንና ጐስቍልናን ይልበሱ።**

**35፡22-26** መዝሙረኛው ያህዌ ሁኔታውን እንደሚያውቅ ይናገራል (መዝ. 10:14፤ 32:8፤ 33:18፤ 34:15፤ ዘጸ. 3፡7)። የጠላቶችን ጥቃት ከማወቁ የተነሣ፣

1. ዝም አትበል – ቢዲቢ 361፣ ኬቢ 357፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ መዝ. 28:1፤ 39:12፤ 83:1፤ 109:1፤ ደግሞም ዕን. 1:13 ላይ ያለውን ማስታወሻ
2. ከእኔ አትራቅ – ቢዲቢ 934፣ ኬቢ 1221፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ መዝ. 10:1፤ 22:11፤ 38:21፤ 71:12

እነዚህን ተጽዕኗዊዎች ሦስት የተለዩ የጸሎት ጥያቄዎች ይከተሏቸዋል (ተተኳሪዎች) ለፍርድ ችሎት (ማለትም፣ "ጽድቅ" "ጉዳይ")።

1. ተነሥ – ቢዲቢ 734፣ ኬቢ 802፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 7:6፤ 44:23፤ 59:4፤ 80:2
2. ንቃ – ቢዲቢ 884፣ ኬቢ 1098፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

3. ፍረድ – ቢዲቢ 1047፣ ኬቢ 1622፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ *መዝ.* 26፡1፤ 43፡1፤ 139፡1፣23፤ ፍርዱ "እንደ ጽድቁ መጠን እንደሆነ" ተገንዘቡ (ዝከ. 31፡1ሐ፤ ሮሜ 4-6፤ ገላትያ 3)

በቀጣዩ ቁጥሮች (35:24ለ-26) ሌሎች ተለጣጣቂ ስድስት ቃል ያልተጠናቀቁዎች በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ ውለዋል።

1. በእኔ ላይ ደስ እንዲሰኙ አትተዋቸው – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ቁ. 24
2. በልባቸውም "እሰይ፣ የልባችን መሻት!" አይበሉ – ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ቁ. 25
3. ደግሞም "ዋጥነው" አይበሉ – ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀበተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ቁ. 25
4. ይፈሩ – ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ቁ. 26
5. ይጎስቁሉ – ቢዲቢ 344፣ ኬቢ 340፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ቁ. 26
6. ኀፍረትንና ጉስቁልናን ይልበሱ – ቢዲቢ 344፣ ኬቢ 340፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ቁ. 26

***መዝሙር ፡ 35፡27-28***

**[27]ጽድቄን የሚወድዱአት ደስ ይበላቸው ሐሴትንም ያድርጉ**
**የባሪያውን ሰላም የሚወድድ**
**እግዚአብሔር ታላቅ ይሁን ዘወትር ይበሉ።**
**[28]ምላሴ ጽድቅህን**
**ሁልጊዜም ምስጋናህን ይናገራል።**

**35፡27-28** እንደገናም አራት ተለጣጣቂ ቃል ተተኳሪዎች አሉ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ።

1. የእኔን ጽድቅ የሚወዱ (ዝከ. 35፡24ሀ) በደስታ ይጩኹ – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 27
2. ሐሤት ያድርጉ (ከቁ. 1 ጋር ትይዩ) – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 27
3. ዘወትር ይበሉ – ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 27
4. እግዚአብሔር ታላቅ ይሁን – ቢዲቢ 152፣ ኬቢ 178፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቁ. 27

**35፡28** የእምነተ-ቢስ ምላስ ሐሰትን፣ አሉባልታን፣ እና ምሬትን ያሰራጫል፣ ነገር ግን የታመነ ተከታይ ምላስ የሚናገረው

1. ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ፣ *መዝ.* 51፡14፤ 71፡15፣24
2. ስለ እሱ ምስጋና ነው

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>*መመሪያ*</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

5. ይህ መዝሙር ያህዌን እንደ ተዋጊ በምናባዊ ምስያ እንዴት ነው የተጠቀመው?
6. መዝሙረኛው ያህዌን የሚጠይቃቸውን ነገሮች ዘርዝር፣ በጠላቶቹ ላይ እንዲያደርግ፣ ቁጥር 4-5 ላይ እና በድጋሚም ቁጥር 24ለ-26 ላይ።
7. "እንዳንተ ማነው?" የሚለው ሐረግ አንድምታው ምንድነው? (ቁ. 10)
8. መዝሙረኛው በወዳጆቹ እንደተካደ የተሰማው ለምንድነው? (ዝከ. ቁ. 13-14)
9. "እሰይ፣ እሰይ" የሚሉት ቃላት አንድምታቸው ምንድነው፣ (ዝከ. ቁ 21፣25)?
10. መዝሙረኛው ለደጋፊዎቹ የሚለምነውን መልካም ነገሮች ዘርዝር፣ ቁ. 27 ላይ።

# መዝሙር 36
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጆት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የሰዎች ክፋት እና የእግዚአብሔር ቸርነት | የሰው ክፋት እና የእግዚአብሔር ፍጽምና | ድብልቅ ዓይነት መዝሙር | የሰዎች ክፋት | የኅጢአተኞች ዓመጸኝነትና እና የእግዚአብሔር ቸርነት |
| ኤምቲ መግቢያ<br>"ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር፣ የእግዚአብሔር ባርያ" | | | 36:1-4 | 36:1 |
| 36:1-4 | 36:1-4 | 36:1-4 | | 36:2-3ሀ |
| | | | የአምላክ መልካምነት | 36:3ለ-6ሀ |
| | | | 36:5-6 | |
| 36:5-9 | 36:5-9 | 36:5-6 | 36:7-9 | |
| | | 36:7-9 | | 36:6ሐ-7 |
| | | | | 36:8-9 |
| | | | 36:10-12 | 36:10-11 |
| 36:10-12 | 36:10-12 | 36:10-12 | | 36:12 |

## የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር ይገልጻል፣ መልካም ያልሆኑ ሰዎችን ቁ. 1-4 ላይ እና ከዚያም ታማኝ ተከታይ ቁ. 7-9 ላይ።

ለ. ያህዌ ተገልጿል፣ ቁ. 5-6 ላይ በአራት ኃይለኛ ገላጭ ስሞች።
5. ቸርነት
6. ታማኝነት
7. ጻድቅነት
8. ፍርድ/ፍትሕ

እነርሱም ያህዌንና ኪዳኑን ይገልጻሉ። እነዚህ ናቸው፣ የእርሱ ዓለም እንዴት መሥራት እንዳለበት ፍላጎቶቹ።

ሐ. ቁጥር 10-12 ለያህዌ የሚደረገውን የማጠቃለያ ጸሎት ያቀርባል፣ መልካሙን ከክፉዎች ተጽዕኖ ለመመከትና ለመርዳት። ወደ ታች የሚጎትተውን
6. የወደቀው ዓለም (ኤፌ. 2:1)
7. የወደቀው ባህል
8. የወደቀው ወዳጅነት (1 ቆሮ. 15:33)
9. የወደቀው እኔነት (ኤፌ. 2:3)

10. ኤፌ. 4፡2 ደግሞ ሰይጣንን ይጨምራል (ማለትም፣ በአየር ላይ ሥልጣን ያለው ገዥ) እሱም ዘወትር እጅግ ብርቱ፣ ቋሚ፣ እና የተሰራጨ። የያህዌ ባሕርይ፣ ቃል፣ እና ጣልቃ ገብነት ብቻ ነው የእኛ ተስፋ።

መ. ሁለት የተለዩ የቃል አጠቃቀሞች በዚህ መዝሙር ላይ ይገኛሉ።
1. ሰዋዊ ክፉ (ማለትም፣ "መተላለፉ የሚናገርበት")፣ ቁ. 1
2. "ቤት" የሚያመለክተው ሁሉንም ፍጥረት ነው ወይም የፍጻሜ ዘመንን መቼት። ቁ. 8-9 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 36፡1-4**

**ለመዘምራን አለቃ የእግዚአብሔር ባሪያ የዳዊት መዝሙር።**
**1ኃጢአተኛ በራሱ የሚያስት ነገርን ይናገራል፥**
**የእግዚአብሔርም ፍርሃት በዓይኖቹ ፊት የለም።**
**2በአንደበቱ ሸንግሎአልና**
**ኃጢአቱ ባገኘችው ጊዜ ይጠላታል።**
**3የአፉ ቃል ግፍና ሽንገላ ነው**
**ማስተዋልን በጎ ማድረግንም ተው።**
**4በመኝታው ጠማማነትን አሰበ**
**መልካም ባልሆነች መንገድ ቆሞአል**
**ክፋትን አይንቃትም።**

**36፡1-4** እነዚህ ቁጥሮች ክፉዎችን ነው የሚገልጹት (ቢዲቢ 959)።
1. ኃጢአተኛ በራሱ የሚያስት ነገርን ይናገራል (LXX፣ ኤምቲ፣ "የእኔ") ልብ (ቢዲቢ 833 ይሄንን የሚጠራው "በርኩስ መንፈስ ሰውኛ የተደረገ")። የመተላለፍ/ዐመጸኝነት ግሥ መዝ. 37:38፤ 51:13፤ ኢሳ. 43:27፤ 59:13፤ 66:24፤ ኤር. 2:8፣29፤ 3:13፤ 33:8 ላይ ጥቅም ላይ የዋለው፣ በኪዳኑ ሕዝብ መሐል ያለውን መተላለፍ/ዓመጸኝነት ለማመልከት ነው። መዝሙረኛው የሚኖረው እንደበታቸው በረከሰ ሰዎች መካከል ነው (ኢሳ. 6፡5፣9-10)።
2. ፍርሃት የለም (ማለትም፣ ድንጋጤ፣ ቢዲቢ 808) የእግዚአብሔር በፊታቸው። የእግዚአብሔር ፍርሃት ማስጠንቀቂያ ተደርጎበታል፣ መዝ. 34፡9፤ 55፡19መ ላይ። ይህ ቁጥር የመዝጊያ ጽሑፍ ነው፣ በብኪ ጽሑፎች የተጠቀሰ፣ እነርሱም የሰው ልጆች ሁ ሁለንተናዊ ኃጢአተኝነት ሮሜ. 3፡18 ላይ።
3. "ሰዋዊ መተላለፍ" ቢሆን ወይም መልካም ያልሆነ ሰው ራሱ ይዋሻል ("የለሰለሰ ንግግር" ቢዲቢ 325፣ ኬቢ 322፣ ሂፊል የተጠናቀቀ) ለራሱ ስለ ገዛ ራሱ በደል።
4. የአፉ ቃል (እሱም ማንነቱን የሚያንጸባርቅ)
ሀ. ክፋት ነው (ቢዲቢ 19)
ለ. የሚያስት (ቢዲቢ 941)
5. እሱ አቁሟል
ሀ. ጠቢብ ከመሆን (ቢዲቢ 968፣ ኬቢ 1328፣ *ሂፊል ያልተወሰነ* አወቃቀር)
ለ. መልካምን ከማድረግ (ቢዲቢ 405፣ ኬቢ 408፣ *ሂፊል ያልተወሰነ* አወቃቀር)
6. እሱም ክፋትን በመኝታው ላይ ያስባል (ሁሉም 36፡4 ላይ ያሉ ግሦች ተተኳሪዎች ናቸው፣ በሂደት ላይ ያለን ድርጊት የሚገልጹ)፣ ምሳ. 4፡16፤ ሚክያስ 2፡1።
7. እሱ መልካም ባልሆነ መንገድ ይራመራል። ሕይወት ባሕርይ የተደረገው እንደ ፈለግ፣ መንገድ፣ ፍኖት መሆኑን አስታውስ። እያንዳንዳችን የትኛው መንገድ እንደሆነ መምረጥ ይኖርብናል፣ ዘዳ. 30:15፣19፤ ማቴ. 7:13-14።
8. እሱ ክፉን አይጸየፍም።

የኪዳኑ ሕዝቦች እንኳ ይፈተናሉ/ይሞከራሉ (ማለትም፣ ሰውኛ የሆነ ዓመጻ) ነገር ግን ገና ስለ ምርጫቸው እና ምርጫቸው ስለሚያስከትለው ውጤት ኃላፊነት አለባቸው!

**መዝሙር ፡ 36፡5-9**

**5አቤቱ፥ ምሕረትህ በሰማይ ነው፥**
**እውነትህም ወደ ደመናት ትደርሳለች።**
**6ጽድቅህም እንደ እግዚአብሔር ተራሮች፥**
**ፍርድህም እጅግ ጥልቅ ናት አቤቱ፥**
**ሰውንና እንስሳን ታድናለህ።**
**7አቤቱ፥ ምሕረትህን እንዴት አበዛህ!**
**የሰው ልጆች በክንፎችህ ጥላ ይታመናሉ።**
**8ከቤትህ ጠል ይጠጣሉ፥**
**ከተድላም ፈሳሽ ታጠጣቸዋለህ።**
**9የሕይወት ምንጭ ከአንተ ዘንድ ነውና**
**በብርሃንህ ብርሃንን እናያለን።**

**36፡5-9** ይህ አንጓ የሚገልጸው የያህዌን ባሕርይና ድርጊቶች ነው፣ ለሕዝቡ ያለውን። ዓመጸኛ የራሱን/የራሷን ምርጫ መርጦ እንደሚኖርበት ሁሉ፣ እንዲሁ ደግሞ የታመኑ ተከታዮች ለያህዌ ፍቅር የሚሰጡትን ምላሽ መቀጠል ይኖርባቸዋል።

1. ያህዌህ ተገልጿል፣ ቁ. 5-6 ላይ እንደ
   ሀ. ቸርነት (ቢ.ዲ.ቢ. 338፣ ማለትም፣ የኪዳን ታማኝነት።፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 5:7 ላይ)
   ለ. ታማኝነት (ቢ.ዲ.ቢ. 53፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 12:1 ላይ)
   ሐ. ጽድቅ (ቢ.ዲ.ቢ. 842፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:5 ላይ)
   መ. ፍርድ (ቢ.ዲ.ቢ. 1048፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9:5-6 ላይ)
   እነዚህ አራቱ ብርቱ፣ ተደጋጋሚ የያህዌ አስተዋጽዖ ናቸው። እነርሱም እርሱ ከሰው ልጆች ጋር የሚያደርገውን ነገር ይዘዋል። ከእነዚህ አስተዋጽዖዎች አኳያ ሰዎች እና በዚህ ምድር ላይ ያለ ሕይወት ሁሉ ተጠብቋል (ቢ.ዲ.ቢ. 446፣ ኬቢ. 448፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቁ)። ኤሎሂም ይሄንን ፕላኔት፣ ሕዝቡን፣ እንስሳቱን፣ እና የፕላኔት ሕይወትን ፈጥሯል፣ ይመግባልም (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፣ መዝ. 1:1 ላይ)።
2. ታማኝ ተከታዮች
   ሀ. በክንፎችህ ጥላ ሥር ያርፋል (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡11-12 ላይ)
   ለ. ከቤትህ ካለው የተትረፈረፈ ነገር እስኪረኩ ይጠጣሉ (ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት መ ወይም 36፡8 ላይ ያለውን ማስታወሻ)
   ሐ. ቤትህ ይኖራቸዋል፣ እንደ
      (1) የሕይወት ምንጭ 2:13፤ 17:13
      (2) ብርሃን (ማለትም፣ እውነት፣ ጤና፣ ደስታ፣ ዝኪ. 18:28፤ 27፤1)

**36፡7 "አቤቱ ጌታ፣ የሰው ልጆች"** ሊሆን የሚችለው "እግዚአብሔር" (ኤሎሂም) እዚህ መጥቀስ ያለበት/የሚጠቅሰው "መሪዎችን" ነው፣ ምክንያቱም ከ"ሰው እና እንስሳት" ጋር ትይዩ ስለሆነ (ማለትም፣ የሁለት ምድብ) 36፡6ሐ። እንደዚያ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ሁለቱ የሰዎች ምድቦች የሚያመለክቱት መሆን ያለበት

1. መሪዎች (ማለትም፣ ፈራጆች ዘጸ. 21፡6፤ መዝ. 82፡6 ወይም መሪዎች መዝ. 29፡1፤ 58፡1)
2. የሚመሩ

አእመቅ፣ የተእመቅ፣ አእቅ፣ እና ኤቢ "አምላክ እና ሰዎች" የሚል የግርጌ ማስታወሻ አላቸው።

**36፡8 "ቤትህ"** በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ መቅደስን አያመለክትም፣ ነገር ግን ዳግም የተፈጠረውን ዔድንን እንጂ (ማለትም፣ "ደስታ" ቢ.ዲ.ቢ. 726፣ ቁ. 8ለ) ወይም የፍጻሜ ዘመን መቼት (ማለትም፣ አዲሱ ዘመን መዝ. 46:4፤ ሕዝ. 47:1-12፤ ኢዩኤል 3:18፤ ራዕ. 22:1-2)።

**መዝሙር ፡ 36፡10-12**

**[10]ምሕረትህን በሚያውቁህ ላይ፥**
**ጽድቅህንም ልባቸው በቀና ላይ ዘርጋ።**
**[11]የትዕቢት እግር አይምጣብኝ፥**
**የኃጢአተኞችም እጅ አያውከኝ።**
**[12]ዓመፃን የሚያደርጉ ሁሉ ከዚያ ወደቁ**
**ወድቀዋል፥ መቆምም አይችሉም።**

**36፡10-12** ይህ የማጠቃለያ አንጓ መዝሙረኛው ለያህዌ የሚያቀርበው ጸሎት ነው፣ በታማኝ ተከታዮች አኳያ (ማለትም፣ "አንተን ለሚያውቁህ፣" ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡6 ላይ)።

1. ቀጥል – ቢ.ዲ.ቢ. 604፣ ኬቢ. 645፣ *ቃል ተተኳሪ*
   ሀ. በቸርነትህ
   ለ. በጽድቅህ
2. አትፍቀድ
   ሀ. የኩራት እግሮች በእኔ ላይ እንዳይመጡ – ቢ.ዲ.ቢ. 97፣ ኬቢ. 112፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   ለ. የኃጢአተኛ እጅ እንዳያውከኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 626፣ ኬቢ. 678፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. ክፉው ይሁንበት
   ሀ. ይውደቅ – ቢ.ዲ.ቢ. 656፣ ኬቢ. 709፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
   ለ. ይውደቅ – ቢ.ዲ.ቢ. 190፣ ኬቢ. 218፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
   ሐ. መነሣት አይሁንለት – ቢ.ዲ.ቢ. 407፣ ኬቢ. 410፣ *ቃል* የተጠናቀቀ (ሦስቱም ግሦች ሁሉ ሞትንና ወደ ሲዖል መውረድን ያመለክታሉ)

የእምነትን ውጤት አስተውሉ (36፡7-8) እና (36፡11-12)። ምርጫዎች ውጤቶች አሏቸው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት _መመሪያ_ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ያሉህን ትርጉሞች ሁሉ አነጻጽር፣ እነርሱም ቁጥር 1ን የሚተረጉሙበትን የተለያዩ መንገዶች አስፍር።
2. የቁጥር 1-4ን ዋነኛ ሐሳብ በገዛ ራስህ ቃላት በአንድ አስረጅ ዓረፍተ ነገር ግለጽ።
3. አራቱ ጠቃሚ ቃላት፣ ቁ. 5፥6 ላይ ያሉት ስለ ሁኔታዊ እና ሁኔታዊ ያልሆነ የብኪ ኪዳናት ጽንሰ-ሐሳብ ምን ይላሉ?
4. ኤሎሂም የሚለው ቃል፣ ቁጥር 7 ላይ ስለ ፈራጆች፣ ወይም የእስራኤል መሪዎች ብሎም ስለ እስራኤል አምላክ መጥቀስ ይችላልን? ለምን?
5. “በከንፎችህ ጥላ ሥር” የሚለው ቃል ስለ እግዚአብሔር በአንስታይ ጾታ የሚያመለክተው ለምድነው? የዚህ ዓይነቶቹ መግለጫዎች አንድምታቸው ምንድነው?
6. ዳዊት ስለ ጠላቶቹ ጥፋት መጸለዩ ላንተ መንፈሳዊ አይመስልህምን?

## መዝሙር 37
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| በእግዚአብሔር የሚታመኑ ደኅንነትና የክፉዎች ጥፋት <u>ኤምቲ መግቢያ</u> የዳዊት መዝሙር | የጻድቅ ውርስ እና የክፉዎች ጥፋት | የክፉዎች ፍርድ ርግጠኝነት /የጥበብ መዝሙር/ | የክፉ እና የመልካም መዳረሻ | የጻድቅ እና የኃጢአተኛ ዕጣ ፈንታ /መስቀልያ/ |
| 37:1-6 | 37:1-2 | 37:1-2 | 3:1-2 | 37:1-2 (*አሌፍ*) |
| | 37:3-4 | 37:3-4 | 37:3-4 | 37:3-4 (*ቤት*) |
| | 37:5-6 | 37:5-6 | 37:5-6 | 37:5-6 (*ጋሜል*) |
| 37:7-11 | 37:7-11 | 37:7 | 37:7 | 37:7 (*ዳሌጥ*) |
| | | 37:8-9 | 37:8-9 | 37:8-9 (*ሂ*) |
| | | 37:10-11 | 37:10-11 | 37:10-11 (*ዋው*) |
| 37:12-15 | 37:12-15 | 37:12-13 | 37:12-13 | 37:12-13 (*ዛይን*) |
| | | 37:14-15 | 37:14-15 | 37:14-15 (*ሄት*) |
| 37:16-22 | 37:16-17 | 37:16-17 | 37:16-17 | 37:16-17 (*ቴት*) |
| | 37:18-20 | 37:18-19 | 37:18-20 | 37:18-19 (*ዮ*) |
| | | 37:20 | | 37:20 (*ኬፍ*) |
| | 37:21-22 | 37:21-22 | 37:21-22 | 37:21-22 (*ላሜድ*) |
| 37:23-26 | 37:23-24 | 37:23-24 | 37:23-24 | 37:23-24 (*ሜም*) |
| | 37:25-26 | 37:25-26 | 37:25-26 | 37:25-26 (*ነን*) |
| 37:27-34 | 37:27-29 | 37:27-29 | 37:27-29 | 37:27-28b (*ሳሜክ*) |
| | | | | 37:28c-29 (*አይን*) |
| | 37:30-31 | 37:30-31 | 37:30-31 | 37:30-31 (*ፒ*) |
| | 37:32-33 | 37:32-33 | 37:32-33 | 37:32-33 (*ዛዲ*) |
| | 37:34-36 | 37:34 | 37:34 | 37:34 (*ቆፍ*) |
| | | 37:35-36 | 37:35-36 | 37:35-36 (*ረሽ*) |
| 37:35-40 | | | | |
| | 37:37-38 | 37:37-38 | 37:37-38 | 37:37-38 (*ሺም*) |
| | 37:39-40 | 37:39-40 | 37:39-40 | 37:39-40 (*ታው*) |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

*ሀ. ይህ መዝሙር ኋላና ፊት እያለ ታማኝ ተከታዮችን የሚያስጠነቅቅና የሚገልጽ፣ እና ታማኝ ያልሆኑትን በመግለጽ መካከል የሚረግጥ ነው። ሥነ-መለኮታዊው ጉዳይ የክፉው ብልጽግና ነው /መዝሙር 73፤ ዕንባቆም።*

ለ. ያህዌ በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ባሕርዩ ተገልጿል። እሱ የታመነውን ይደግፋል፣ እምነት የሌለውን ያጠፋል።

ሐ. ይህ መስቀልያ መዝሙር ነው። እያንዳንዱ የተመለከተ ፊደል ሁለት ቁጥሮች አሉት /ማለትም፣ 4 መስመሮች/ ከቆፍ በቀር፣ 37፡34፣ እሱም 3 መስመሮች ያሉት።

መ. የዚህ መዝሙር ሥነ-መለኮት፣ ምድርን ስለመውረስ /ማለትም፣ ከነአን/ ስለ ብልጽግና የተመሠረተው ዘፍ. 12፡1-3 ላይ ነው /የያህዌ መነሻ ጥሪ እና ተስፋ ለአብርሃም/፣ እሱም በሙሴ ወደ ሙሴ ኪዳን የዳበረ። እሱም ለታዛዦች በረከት ለማይታዘዙት ደግሞ ርግማን አለው /ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30 ለተሻለ ማጠቃለያ/።

እግዚአብሔር ራሱን ለዓለም መግለጽ ይፈልጋል በልዩ የኪዳን ሕዝቡ በእስራኤል በኩል።እስራኤል የተፈለገው የእርሱን ጸጋ፣ ምሕረት፣ እና ፍቅር ለመግለጽ ነበር፣ በብልጽግናውና በመልካም ባህሉ። ከታሪካዊ መጻሕፍት ግልጽ እንደሆነው /ማለትም፣ ኢያሱ — 2 ነገሥት/፣ የእስራኤል አለመታዘዝ ይህን ዓላማ አበላሸው። እስራኤል ተፈረደበት፣ ኪዳኑም ተሰበረ /ማለትም፣ ግዞት/። ስለዚህ፣ ያህዌህ "አዲስ ኪዳን" ለማውጣት ተገደደ (ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝ. 36፡22-38) በራሱ ጸጋና ድርጊት ላይ ተመሥርቶ፣ በወደቀው ሰው መታዘዝ ላይ ሳይሆን /ማለትም፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል፣ በአኪ የሰፈረው/። በዚህ አዲስ ኪዳን ለብሔረ-እስራኤል የተገቡት ተስፋዎች ተሰረዙ! ከታች ልዩ ርዕስ አኑሬአለሁ፣ ይሄንን ለውጥ ለመዘገብ የሚሞክር!

## ልዩ ርዕስ ፡ የፍፃሜ ጊዜያት ክስተቶች ለምን አከራካሪ ሆኑ

***የመጀመሪያው ተቃርኖ*** (የብኪ ዘራዊ፣ ብሔራዊ፣ እና መልክዓ ምድራዊ ምድቦች በተቃርኖ አማኞች ሁሉ በምድር ሁሉ ላይ ያሉ)

የብኪ ነቢያት የሚተነብዩት የአይሁድን መንግሥት መመለስ፣ በፍልስጥኤም ኢየሩሳሌምን ማዕከል አድርጎ ሲሆን እዚያም የዓለም ሕዝቦች ሁሉ ዳዊታዊውን ገዥ ለማመስገንና ለማገልገል፤ ነገር ግን ኢየሱስም ሆነ የአኪ ሐዋርያት በዚህ አጀንዳ ላይ ፈጽሞ አላተኮሩም። ብኪ ተመስጧዊ አይደለምን (ማቴ. 5፡17-19)? የአኪ ጸሐፍት ዋነኞቹን የፍጻሜ ዘመን ሁነቶች ገድፈዋቸዋልን?

በርካታ የመረጃ ምንጮች አሉ ስለ ፍጻሜው ዘመን ዓለም።

1. የብኪ ነቢያት (ኢሳይያስ፣ ሚክያስ፣ ሚልክያስ)
2. የብኪ የፍጻሜ ዘመን ጸሐፍት (ሕዝቅኤል 37-39፤ ዳንኤል 7-12፤ ዘካርያስ)
3. በይነ-ኪዳናዊ፣ ካኖናዊ ያልሆኑ የአይሁድ የፍጻሜ ዘመን ጸሐፍት (ለምሳሌ 1 ሔኖክ፣ እሱም ይሁዳ ላይ የተጠቀሰ)
4. ኢየሱስ ራሱ (ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13፤ ሉቃስ 21)
5. የጳውሎስ ጽሑፎች (1 ቆሮንቶስ 15፤ 2 ቆሮንቶስ 5፤ 1 ተሰሎንቄ 4-5፤ 2 ተሰሎንቄ 2)
6. የዮሐንስ ጽሑፎች (1 ዮሐንስ እና ራዕይ)።

እነዚህ ሁሉ የፍጻሜ ዘመንን አጀንዳ በግልጽ ያስተምራሉን (ሁነቶችን፣ ዜና መዋዕልን፣ ሰዎችን)? እንደዚያ ካልሆነ፣ ለምን? ሁሉም ተመስጧዊ አይደሉምን (ከአይሁድ በይነ-ኪዳናዊ ጽሑፎች በተቀር)?

መንፈስ ቅዱስ እውነትን ለብኪ ጸሐፍት ገልጾላቸዋል፣ ሊገነዘቧቸው በሚችሉት ቃላትና ምድቦች (ዘውጎች)። ሆኖም ቀጣይነት ባለው መገለጥ መንፈስ ቅዱስ እነዚህን የፍጻሜ ዘመን ጽንሰ-ሐሳቦች ወደ ሁለንተናዊ ዳርቻ አስፋፍቷቸዋል ("የክርስቶስ ምሥጢር፣" ኤፌ. 2፡11-3፡13። ልዩ ርዕስ ተመልከት 10፡7 ላይ)። እዚህጋ አንዳንድ ጠቃሚ ምሳሌዎች ይገኛሉ፡

1. የኢየሩሳሌም ከተማ በብኪ ለእግዚአብሔር ሕዝብ በዘይቤነት ጥቅም ላይ ውሏል (ጽዮን)፣ ነገር ግን አመላካችነቱ ወደ አኪ ነው፣ እግዚአብሔር በንስሐ የሚመለሱትን፣ አማኝ ሰዎች ሁሉ እንደሚቀበል ለመግለጽ ነው፣ (አዲሲቷ ኢየሩሳሌም የራዕይ 21፡22)። ሥነ-መለኮታዊው ጥሬያዊ፣ አካላዊ ከተማ ወደ አዲስ የእግዚአብሔር ሕዝብ መስፋፋት (አማኝ አይሁድ እና አሕዛብ) ለእግዚአብሔር ተስፋ እንደ ጥላ (ንግር) ሆኗል፣ የወደቀውን የሰው ልጅ ለመዋጀት፣ ዘፍጥረት 3፡15 ላይ፣ ምንም ዓይነት አይሁድ ወይም የአይሁድ ዋና ከተማ ባልነበረበት ሰዓት እንኳ። የአብርሃም ጥሪ እንኳ ቢሆን (ዘፍ. 12፡1-3) አሕዛብን ያካትታል (ዘፍ. 12፡3፤ ዘጸ. 19፡5)።
2. በብኪ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጠላቶች የጥንታዊው ቅርብ ምስራቅ አካባቢ ሕዝቦች ነበሩ፣ ነገር ግን በአኪ እነርሱ ወደማያምኑት ሁሉ፣ ጸረ-እግዚአብሔር፣ በሰይጣናዊ ተመስጦ ውስጥ ወዳሉት ሕዝቦች ተስፋፍተዋል። ውጊያው ከመልክዓ-ምድራዊ፣ ክልላዊ ግጭት ወደ ዓለም-አቀፍ፣ ሁለንተናዊ ግጭት ተሸጋግሯል (ቆላስይስ)።
3. የምድር (መሬት) ተስፋ፣ እሱም በብኪ <u>እጅግ</u> ዋነኛ የሆነ (የዘፍጥረቱ የአባቶች ተስፋ፣ ዘፍ. 12፡7; 13፡15; 15፡7,15; 17፡8) አሁን ለመላው ምድር (ዓለም) ሆኗል። አዲሲቷ ኢየሩሳሌም ዳግም ወደ ተፈጠረችው ምድር ወርዳለች፣ ለቅርብ ምስራቅ ወይም በማያካትት መልኩ ሳይሆን (ራዕይ 21-22)።
4. እየተስፋፉ ያሉት ሌሎች የብኪ ትንቢታዊ ጽንሰ-ሐሳብ ምሳሌዎች
   ሀ. የአብርሃም ዘሮች አሁን በመንፈሳዊ የተገረዙት ናቸው (ሮሜ. 2፡28-29)
   ለ. የኪዳን ሕዝብ አሁን አሕዛብን ያካትታል (ሆሴ. 1፡10; 2፡23, ሮሜ. 9፡24-26 ላይ የተጠቀሰ; ደግሞም ሌዋ. 26፡12; ዘጸ. 29፡45, 2 ቆሮ. 6፡16-18 ላይ የተጠቀሰ እና ዘጸ. 19፡5; ዘዳ. 14፡2, ቲቶ 2፡14 ላይ የተጠቀሰ)
   ሐ. ቤተ-መቅደሱ አሁን ኢየሱስ ነው (ማቴ. 26፡61; 27፡40; ዮሐንስ 2፡19-21) በእርሱ በኩልም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት (1 ቆሮ. 3፡16) ወይም ግለሰብ አማኝ (1 ቆሮ. 6፡19)
   መ. እስራኤል እና የእርሱም ባሕርያት የሆኑ ገላጭ የብኪ ሐረጋት እንኳ አሁን ሁሉንም የእግዚአብሔር ሕዝብ ያመለክታሉ (ማለትም፣ "እስራኤል," ሮሜ. 9፡6; ገላ. 6፡16, ማለትም፣"የካህናት መንግሥት፣" 1 ጴጥ. 2፡5, 9-10; ራዕ. 1፡6)

ትንቢታዊው ማሳያ (ሞዴል) ተፈጽሟል፣ ተስፋፍቷል፣ እናም አሁን እጅግ አካታች ነው። ኢየሱስና ሐዋርያዊ ጸሐፍት የፍጻሜ ዘመንን እንደ ብኪ ነቢያት ተመሳሳይ በሆነ መንገድ አላቀረቡም (ማርቲን ዋይንጋርደን፣ *ቀጣዩ መንግሥት በትንቢትና በፍጻሜ*)። ዘመናዊዎቹ ተርጓሚዎች፣ እነርሱም የብኪን ሞዴል በጥሬው ወይም በቀጥታ ለመውሰድ የሚሞክሩ ራዕይን ያጣምማሉ፣ ወደ ዓይነተኛ የአይሁድ መጽሐፍ፣ እናም ፍችውን ይገፋታል፣ ወደ ደቀቀ፣ አሻሚ የኢየሱስና የጳውሎስ ሐረጎች! የአኪ ጸሐፍት የብኪ ነቢያትን አይቃረኑም፣ ነገር ግን የእነርሱን

የመዳረሻና ሁለንተናዊ አንድምታ ያመለክታሉ እንጂ። ምንም ዓይነት የተደራጀ፣ ሎጂካዊ ስልት የለም፣ ለኢየሱስም ሆነ ለጳውሎስ ለፍጻሜ ዘመን ሥነ-መለኮት (አስተምህሮ)። የእነርሱ ዓላማ በቅድሚያ የመዋጀት ወይም የእረኝነት ነው።

ሆኖም፣ በአኪ እንኳ ቢሆን ተቃርኖ አለ። ግልጽ የሆነ ስልት የተበጀላቸው የፍጻሜ ዘመን ሁነቶች የሉም። በብዙ መንገዶች ራዕይ በሚያስገርም መልኩ የብኪን ጠቃሾች ይጠቀማል፣ ፍጻሜን ለመግለጽ፣ በኢየሱስ ትምህርቶች ፈንታ (ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13)! እሱም የሕዝቅኤልን፣ ዳንኤልን፣ እና ዘካርያስን ጽሑፋዊ ዘውግ መነሻ ይከተላል፣ ነገር ግን በበይነ-ኪዳናዊ ጊዜ የጎለበቱትን (የአይሁድ የፍጻሜ ዘመን ሥነ-ጽሑፍ)። ይህም የዮሐንስ የማያያዣ መንገድ ሊሆን ይችላል፣ ብሉዩንና አዲሱን ኪዳናት። እሱም የረጅም ዕድሜ ፈርጅን ያመለክታል፣ የሰውን ዓመጸኝነትና የእግዚአብሔርን የመዋጀት ቁርጠኝነት! ነገር ግን መታየት ያለበት፣ ምንም እንኳ ራዕይ የብኪ ቋንቋን፣ ሰዎችን፣ እና ሁነቶችን ቢጠቀምም፣ እሱ ዳግም የሚተረጉማቸው በአንደኛው ክፍለ-ዘመን ሮም አንጻር ነው (ራዕ. 1፡7)።

***ሁለተኛው ተቃርኖ*** (አሀዳዊነት አልያም አንድ የተመረጠ ሕዝብ)

መጽሐፍ ቅዱሳዊው አጽንዖት አንድ አካላዊ፣ መንፈሳዊ፣ ፈጣሪ-ተቤዢ፣ አምላክ ነው (ዘጸ. 8፡10፤ ኢሳ. 44፡24፤ 45:5-7,14,18,21-22; 46:9; ኤር. 10:6-7)። የብኪ የተለየነት፣ በገዛ ራሱ ቀን አሀዳዊነቱ ነው። ሁሉም የአካባቢው ሕዝቦች ባለ ብዙ አማኞች ነበሩ። የእግዚአብሔር አንድነት የብኪ ራዕይ እምብርት ነው (ዘዳ. 6፡4)። ፍጥረት በእግዚአብሔር እና በሰው ልጅ መካከል ላለው ኅብረት ዓላማ መድረክ ነው፣ በእርሱ መልክና አምሳል ለተሠራው (ዘፍ. 1፡26-27)። ሆኖም፣ የሰው ልጅ ዓመጸ፣ በእግዚአብሔር ፍቅር፣ መሪነት፣ እና ዓላማ ላይ ኃጢአትን ሠራ (ዘፍጥረት 3)። የእግዚአብሔር ፍቅር እና ዓላማ እጅግ ብርቱ እና ርግጠኛ ነበር፣ የወደቀውን ሰው ለመዋጀት በገባው ቃል (ዘፍ. 3፡15)!

ተቃርኖው የሚነሣው እግዚአብሔር አንድን ሰው፣ አንድን ቤተሰብ፣ አንድን ሕዝብ ለመጠቀም ሲመርጥ ነው፣ ቀሪውን የሰው ልጅ ለመድረስ። እግዚአብሔር አብርሃምንና አይሁድን እንደ ካህናት መንግሥት መምረጡ (ዘጸ. 19፡4-6) ኩራትን አመጣ፣ ከአገልግሎት ይልቅ፣ አለማካተትን በማካተት ፈንታ። እግዚአብሔር አብርሃምን መጥራቱ ሆን ተብሎ የሰው ልጆችን ሁሉ መባረክን አካተተ (ዘፍ. 12፡3)። መታወስና አጽንዖት መሰጠት የሚገባው የብኪ መመረጥ ለአገልግሎት መሆኑ ነው፣ ለመዳን ሳይሆን። እስራኤል ሁሉ ከእግዚአብሔር ጋር ፈጽሞ ልክ አልነበረችም፣ ፈጽሞ ዘላለማዊ ደኅንነት አልነበራትም፣ በራሷ የመወለድ መብት ብቻ ላይ በመመሥረት (ዮሐንስ 8፡31-59፤ ማቴ. 3፡9)፣ ነገር ግን በግል እምነት እና መታዘዝ እንጂ (ዘፍ. 15፡6፣ ሮሜ 4 ላይ የተጠቀሰ)። እስራኤል ተልዕኮዋን አጥታለች (አሁን ቤተ ክርስቲያን የካህናት መንግሥት ነች፣ ራዕ. 1፡6፤ 2 ጴጥ. 2፡5፣9)፣ ኃላፊነት የቀያየረ፣ ወደ መታደል፤ አገልግሎት ወደ ወደ ተለየ አቋም! እግዚአብሔር አንዱን መረጠ፣ ሁሉንም ለመምረጥ!

***ሦስተኛው ተቃርኖ*** (ሁኔታዊ ኪዳናት አልያም ሁኔታዊ ያልሆኑ ኪዳናት)

በሁኔታዊ እና ሁኔታዊ ባልሆኑ ኪዳናት መካከል ሥነ-መለኮታዊ ተቃርኖ ወይም አያዎ (ፓራዶክስ) አለ። ርግጠኛና የታመነ የሆነው የእግዚአብሔር የመዋጀት ዓላማ/ዕቅድ ሁኔታዊ ያልሆነ መሆኑ ነው (ዘፍ. 15፡12-21)። ሆኖም፣ ኃላፊነት የተሞላው የሰው ምላሽ ግን ዘወትር ሁኔታዊ ነው!

“ይህ ከሆነ… ከዚያም” የሚለው ፈርጅ በሁለቱም በብኪም ሆነ በአኪ ላይ ይከሰታል። እግዚአብሔር የታመነ ነው፤ የሰው ልጅ ያልታመነ ነው። ይህ ተቃርኖ ብዙ ውዥንብር ፈጥሯል። ተርጓሚዎች በአንደኛው “የግራ አጋቢው ቀንድ” ላይ ብቻ ሆን ብለው አተኩረዋል፣ የእግዚአብሔር ታማኝነት ወይም የሰው ጥረት፣ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት ወይም የሰው ነጻ ፍቃድ። ሁለቱም መጽሐፍ ቅዱሳዊና አስፈላጊ ናቸው።

ይኽም ከፍጻሜው ዘመን ጋር ይዛመዳል፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ከሰጠው ተስፋ ጋር። እግዚአብሔር እሱን ተስፋ ከሰጠ፣ ያ ያበጀዋል! እግዚአብሔር በተስፋዎቹ ታስሯል፤ መልካም ስሙ ተካቶበታል (ሕዝ. 36፡22-38)። ሁኔታዊ ያልሆነውና ሁናታዊ የሆነው ኪዳን በክርስቶስ ተጋጥመዋል (ኢሳይያስ 53)፣ እስራኤል ሳይሆን! የእግዚአብሔር የመዳረሻ ታማኝነት ንስሐ በሚገቡና በሚያምኑት ሁሉ መዋጀት ላይ ዐርፏል፣ በአባትህ/እናትህ ማንነት ላይ ሳይሆን! ክርስቶስ፣ እስራኤል ሳይሆን፣ ለሁሉም የእግዚአብሔር ኪዳናት እና ተስፋዎች ቁልፍ ነው። ሥነ-መለኮታዊ ቅንፍ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ካለ፣ ቤተ ክርስቲያን አይደለችም፣ እስራኤል እንጂ (ሐዋ. 7 እና ገላትያ 3)።

የዓለም የወንጌል አዋጅ ተልዕኮ ወደ ቤተ-ክርስቲያን ተዛውሯል (ማቴ. 28፡19-20፤ ሉቃስ 24፡47፤ ሐዋ. 1፡8)። እሱ አሁንም ሁኔታዊ ኪዳን ነው! ይህ ማለት እግዚአብሔር ሙሉ ለሙሉ እስራኤልን ትቶታል የሚል አንድምታ ለመስጠት አይደለም (ሮሜ. 9-11)። ለፍጻሜው ዘመን <u>አማኝ</u> እስራኤል ስፍራና ዓላማ ሊኖር ይችላል (ዘካ. 12፡10)።

***አራተኛ ተቃርኖ*** (የቅርብ ምስራቅ ጽሑፋዊ ማሳያዎች (ሞዴሎች) አልያም ምዕራባዊ ማሳያዎች)

ዘውግ ዓይነተኛ ነገር ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስን በአግባቡ ለመተርጎም። ቤተ-ክርስቲያን እየዳበረች የመጣችው በምዕራባዊ (ግሪክ) ባህላዊ መቼት ነው። ምስራቃዊ ሥነ-ጽሑፍ በአብዛኛው ዘይቤአዊ፣ ቅኔአዊ እና ተምሳሊታዊ ነው፣ ከዘመናዊው ምዕራባዊ ሥነ-ጽሑፋዊ ማሳያ ባህል ይልቅ። እሱም የሚያተኩረው በሕዝቦች፣ ግጭቶች፣ እና ሁነቶች ላይ ነው፣ ከአጭር እይታዊ የእውነት ማመላከቻ ይልቅ። ክርስቲያኖች ኃጢአትን ሠርተዋል፣ የራሳቸውን ታሪክ እና ጽሑፋዊ ሞዴሎች በመጠቀማቸው፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ትንቢት ለመተርጎም (ሁለቱንም ብኪንና አኪን)። እያንዳንዱ ትውልድ እና መልክዓ ምድራዊ አሀድ የየራሱን ባህል፣ ታሪክ፣ እና ጥሬአዊነት ተጠቅሟል፣ ራዕይን ለመተርጎም። እያንዳንዳቸው ተሳስተዋል! እሱም መታበይ ነው፣ ዘመናዊው ምዕራባዊ ባህል የመጽሐፍ ቅዱስ ትንቢት አትኩሮት ነው ብሎ ማሰብ!

ዋነኛው ተመስጧዊ ደራሲ ለመጻፍ የመረጠው ዘውግ ከአንባቢው ጋር የተደረገ ጽሑፋዊ ውል ነው። የራዕይ መጽሐፍ ታሪካዊ ትርክት አይደለም። እሱ የመልእክቶች (ምዕራፍ 1-3)፣ ትንቢት፣ እና ባብዛኛው የፍጻሜ ዘመን ሥነ-ጽሑፍ ድብልቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ዋነኛው ደራሲ ሊል ከፈለገው በላይ እንዲል ማድረግ የተሳሳተ ነው፣ ልክ ሊል ከፈለገው አሳንሶ እንደ ማድረግ! የተርጓሚዎች ግትርነትና ቀኖናዊነት እጅግ ተገቢ ያልሆነ ነው፣ እንደ ራዕይ በመሳሰሉ መጻሕፍት ላይ።

ቤተ-ክርስቲያን ፈጽሞ አልተስማማችም በራዕይ ተገቢ የሆነ ትርጓሜ ላይ። እኔን የሚገደኝ ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ መስማትና መያዝ እንጂ ጥቂት የተመረጠ ክፍልን (ሎችን) አይደለም። የመጽሐፍ ቅዱስ ምስራቃዊ የአስተሳሰብ ቅንብር እውነትን የሚያቀርበው ተቃርኖ-ሞል በሆኑ ጥንዶች አማካኝነት ነው። የእኛ ምዕራባዊ ዝንባሌ ወደ ሎጂካዊ እውነታ የሚያደላው ዋጋ የሌለው አይደለም፣ ነገር ግን ሚዛናዊ አይደለም እንጂ! እንደማስበው፣ ማድረግ የሚቻለው ቢያንስ ራዕይን በመተርጎም ላይ አንዳንዱን ውጤት የሌለበትን ነገር መተው እንደሚገባ ነው፣ የመለወጥ ዓላማውን በማጤን፣ ለቀጣዩ አማኝ ትውልድ። በአብዛኞቹ ተርጓሚዎች ዘንድ ግልጽ የሆነው፣ ራዕይ መተርጎም ያለበት በገዛ ራሱ ቀንና ዘውግ አኳያ ነው። ታሪካዊ አገባብ በራዕይ ላይ መያዝ ያለበት የመጀመሪያዎቹ አንባቢዎች ምን እንደያዙ፣ ምን እንደተረዱ ነው። በብዙ መንገዶች ዘመናዊዎቹ ተርጓሚዎች የአብዛኞቹን የመጽሐፉን ተምሳሌቶች ፍች እንዳላገኟቸው ነው። የራዕይ መነሻ ዋነኛ ግፊት በስደት ላይ የነበሩትን አማኞች ማበረታታት ነው። እሱም እግዚአብሔር ታሪክን እንደሚቆጣጠር ያሳያል (የብኪ ነቢያት እንዳደረጉት ሁሉ)፤ እሱም የሚያስረግጠው

ታሪክ ወደ ተቀጠረ ፍጻሜ ስፍራ፣ ፍርድ ወይም ባርኮት ማምራቱን ነው (በብኪ ነቢያት እንደነበረው)። እሱም በአንደኛ ክፍለ-ዘመን አይሁድ የፍጻሜያዊ ቃላት የእግዚአብሔርን ፍቅር፣ መገኘት፣ ኃይል፣ እና ሉዓላዊነት ያስረግጣል!

እሱም በእነዚህ ተመሳሳይ ሥነ-መለኮታዊ መንገዶች ይሠራል፣ ለእያንዳንዱ አማኝ ትውልድ። እሱም ሁለንተናዊውን ትግል ያሳያል፣ የመልካምንና የክፉን። የአንደኛው ክፍለ-ዘመን ዝርዝር ጠፍቶብን ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ኃይለኛው፣ የሚያበረታታው እውነት ሳይሆን። ዘመናዊዎቹ፣ ምዕራባዊ ተርጓሚዎች የራዕይን ዝርዝሮች ወደ ራሳቸው ዘመነኛ ታሪክ ለመግፋት ይሞክራሉ፣ የሐሰተኛ ትርጕሞች ፈርጅ እንደቀጠለ ነው!

በርግጥ ሊሆን ይችላል፣ የመጽሐፉ ዝርዝር ዳግመኛ ባስገራሚ መልኩ ጥሬአዊ መሆኑ (በብኪ እንደ ተደረገው፣ ከክርስቶስ ልደት፣ ሕይወት፣ እና ሞት ጋር በተያያዘ) ለመጨረሻው የአማኞች ትውልድ፣ መታረድ እንደገጠማቸው፣ በጸረ-እግዚአብሔር መሪ (2 ተሰሎንቄ 2) እና ባህል። የእነዚህን የራዕዩን ጥሬአዊ ፍጻሜዎች ማንም ማወቅ አይችልም እስከ ኢየሱስ ቃላት ድረስ (ማቴዎስ 24፤ ማርቆስ 13፤ እና ሉቃስ 21) እና ጳውሎስ (1 ቆሮንቶስ 15፤ 1 ተሰሎንቄ 4-5፤ እና 2 ተሰሎንቄ 2) ደግሞም ከታሪክ አኳያ ማስረጃ ሆኗል። ግምት፣ መላምት፣ እና ቀኖናዊነት ሁሉም ተገቢ አይደሉም። የፍጻሜ ዘመን ሥነ-ጽሑፍ ይሄንን ተጣጣፊነት ይፈቅዳል። እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣ ስለ ምናቦች እና ምስያዎች፣ እነርሱም ታሪካዊ ትርክትን አልፈው ስለሚሄዱ! እግዚአብሔር እየተቆጣጠረ ነው፤ እሱ ይገዛል፤ እሱ ይመጣል!

አብዛኞቹ ዘመናዊ ሐተታዎች የዘውጉን ነጥብ ስተውታል! ዘመናዊዎቹ ምዕራባዊ ተርጓሚዎች ዘወትር የሚሹት ግልጽ፣ ሎጂካዊ የሥነ-መለኮት ሥልትን ነው፣ አሻሚ፣ ተምሳሊታዊ፣ ድራማዊ ዘውግ ከሆነ ከአይሁድ የፍጻሜ ዘመን ሥነ-ጽሑፍ ይልቅ። ይህ እውነት ደኅና ተደርጎ ተገልጿል፣ በራልፍ ፒ. ማርቲን ዘገባ ላይ፣ "የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ አገባቦች፣" በሚለው፤ በመጽሐፉ *የአዲስ ኪዳን ትርጓሜ*፣ በአይ. ሃዋርድ ማርሻል የተዘጋጀ፡

"የዚህን ጽሑፍ ድራማዊ ጥራት እስካልተገነዘብን ድረስ እና ቋንቋ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል መለስ ብለን እስካላሰብን ድረስ፣ ሃይማኖታዊ እውነትን ለመግለጫ መሣርያነት፣ አፖካሊፕስን መረዳታችንን በእጅጉን እንስታለን፣ እናም ቅጅዎቹን በስሕተት ለመተርጎም እንሞክራለን፣ እንደ ጥሬአዊ ዝርው መጽሐፍ እሱም ለተገላጭ ሁነቶች እና ታሪካዊ ቀንን በመግለጽ ላይ እንደሚያተኩር። ሁለተኛውን አካሄድ መሞከር ወደ ሁሉም ዓይነት የትርጓሜ ችግሮች መጣደፍ ማለት ነው። እጅግ የምር በሆነ መልኩም እሱ የአፖካሊፕስን ሁነኛ ፍች እስከ ማዛባት ሊያመራ ይችላል፣ እናም የዚህን የአዲስ ኪዳን ክፍል ታላቅ ዋጋ እስከ መሳት ያደርሳል፣ እንደ ድራማዊ ማስረገጫ፣ በአፈ-ታሪካዊ ቅኔ ቋንቋ፣ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት በክርስቶስ እና የእርሱ ገዥነት አያዎ (ፓራዶክስ) ብርታትን እና ፍቅርን የደባለቀ (ዝከ. 5፥5፣6፤ አንበሳው በጉ ነው)" (ገጽ 235)።

ደብልዩ. ራንዶልፍ ቴት በመጽሐፉ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ትርጓሜዎች ላይ እንዲህ ብሏል፡

"የትኛውም ሌላ የመጽሐፍ ቅዱስ ዘውግ እጅግ ስሜታዊ በሆነ መልኩ አልተነበበም፣ በእነዚህ ዓይነት በሚጫጫን ውጤት፣ እንደ አፖካሊፕስ፣ በተለይም የዳንኤልና የራዕይ መጻሕፍት። ይህ ዘውግ አጥፊ በሆነ የተዛባ ትርጉም ታሪክ ተጎድቷል፣ የእርሱን ጽሑፋዊ መልኮች፣ መዋቅር፣ እና ዓላማ አዛብቶ ከመረዳት የተነሣ። እሱ እጅግ አጠንክሮ ከያዘው በቶሎ የሚሆነው ይገለጥ ዘንድ ከሚለው፣ አፖካሊፕስ እንደ ታተመ የመንገድ ካርታ ወደፊት ስለሚሆነው የሚገልጽ አመለካከት ተደርጎ ተወስዷል። በዚህ አመለካከት ላይ ያለ አሳዛኝ እንከን፣ የመጻሕፍቱ የማጣቀሻ ቅንብብ የአንባቢው ዘመነኛ ዕድሜ ነው፣ የደራሲው ሳይሆን፣ የሚል ግምት ነው። ይህ የተሳሳተ ምሪት ያለው የአፖካሊፕስ አገባብ (በተለይም ራዕይ) ሥራውን የሚይዘው እንደ ምሥጢራዊ ጽሑፍ ነው፣ በዚያም ዘመነኛ ሁነቶች የጽሑፉን ተምሳሌት ለመተርጎም ጥቅም ላይ እንደዋለ... አንደኛ፣ ተርጓሚው መገንዘብ የሚኖርበት አፖካሊፕቲክ መልእክቱን የሚያስተላልፈው በተምሳሊታዊ መሆኑን ነው። ተምሳሊትን በጥሬው መተርጎም፣ ዘይቤአዊ ሆኖ ሳለ፣ እንዲያው አዛብቶ መተርጎም ነው። ጉዳዩ፣ የአፖካሊፕቲክ ሁነቶች ታሪካዊ መሆናቸው አይደለም። ሁነቶቹ ታሪካዊ ሊሆኑ ይችላሉ፤ በርግጥም ሊሆኑ ይችላሉ፣ ወይም ሆነው ይሆናል፣ ነገር ግን ደራሲው ሁነቶቹን የሚያቀርበውና ፍችዎቹን የሚያስተላለፈው በምስያዎችና በማሳያ ነው" (ገጽ 137)።

ከመጽሐፍ ቅዱስ ምናባዊ መዝገበ-ቃላት፣ በራይከን የተዘጋጀ፣ ዊልሆስት እና ሎንግማን III፡

"የአሁኑ ዘመን አንባቢዎች ይህ ዘውግ ዘወትር እንቆቅልሽ እንደሆነባቸውና ግራ እንዳጋባቸው ነው። ያልተጠበቀ ምስል ከሳች ምናባዊነትና ከዚህ ዓለም ውጭ የሆነ ልምምዶች ያልተለመዱና ተንጋግተው የሚደርሱ ሆነዋል፣ ባብዛኛው የቅዱስ ቃሉ ክፍሎች። ይህንን ሥነ-ጽሑፍ በፊት ለፊት ገጽታው እንዳለ መውሰድ ብዙዎቹ አንባቢዎች ከመንገድ እንዲወጡ አድርጓቸዋል፣ 'ምን መቼ ይደርሳል' የሚለውን ለመወሰን፣ ይህም፣ የአፖካሊፕቲክን ሁነኛ መልእክት መሳትን ያስከትላል" (ገጽ 35)።

**አምስተኛ ተቃርኖ** (የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን እንደሆነ አልያም ገና ለወደፊት)

የእግዚአብሔር መንግሥት አሁን ነው፣ ሆኖም ገና ወደፊት። ይህ ሥነ-መለኮታዊ ፓራዶክስ (አያዎ) በፍጻሜ ዘመን ነጥብ ላይ ትኩረትን አግኝቷል። አንዱ ለእስራኤል ስለ ተነገሩት የብኪ ትንቢቶች ጥሬአዊ ፍጻሜን ብቻ የሚጠብቅ ከሆነ፣ እንግዲያውስ መንግሥቱ የሚሆነው ባብዛኛው የእስራኤል መመለስ ነው፣ ወደ መልክዓ ምድራዊ ስፍራ እና ሥነ-መለኮታዊ ቅድመ-ልዕልና ነው! ይህም የግድ የሚሆነው፣ ቤተ-ክርስቲያን በምሥጢር ትነጠቃለች፣ ምዕራፍ 5 ላይ እናም ቀሪዎቹ ምዕራፎች ከእስራኤል ጋር የተያያዙ ናቸው (ግን ራዕ. 22፥16ን ተመልከቱ።)።

ሆኖም፣ አትኩሮቱ በብኪው ተስፋ መሲሕ መንግሥት ምርቃት ከሆነ፣ እንግዲያውስ እሱ በክርስቶስ የመጀመሪያ ምጽአት ተፈጽሟል፣ እናም ከዚያም አትኩሮቱ የክርስቶስ ሥጋዌ (የመለኮት ሥጋ መልበስ)፣ ሕይወት፣ ትምህርት፣ ሞት፣ እና ትንሣኤ ላይ ይሆናል። ሥነ-መለኮታዊው አጽንዖት የአሁኑ ደኅንነት ነው። መንግሥቱ መጥቷል፣ ብኪ በክርስቶስ ለሁሉ ደኅንነት ራሱን ማቅረብ ተፈጽሟል፣ በጥቂቶች ላይ በሺህ ዓመት ንግሥና ሳይሆን!

በርግጠኝነት እውነት ነው፣ መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ሁለቱም የክርስቶስ ምጽአቶች መናገሩ፣ ነገር ግን አጽንዖቱ የሚደረገው የቱጋ ነው? ለእኔ የሚመስለኝ፣ አብዛኞቹ የብኪ ትንቢቶች፣ በመጀመሪያው ምጽአት ላይ ነው የሚያተኩሩት፣ የመሲሑ መንግሥት መመሥረት (ዳንኤል 2)። በብዙ መንገዶች ይህ ምስያ ነው፣ ለእግዚአብሔር ዘላለማዊ ገዥነት (ዳንኤል 7)። በብኪ አትኩሮቱ በእግዚአብሔር ዘላለማዊ ገዥነት ላይ ነው፣ እናም የዛ ግዛት መገለጫ መሣርያው የመሲሑ አገልግሎት ነው (1 ቆሮ. 15፥26-27)። ጥያቄው የትኛው እውነት ነው አይደለም፤ ሁለቱም እውነት ናቸው፣ ግን አጽንዖቱ የት ነው? መባል የሚኖርበት አንዳንድ ተርጓሚዎች እጅግ የሚያተኩሩት በመሲሑ የሺህ ዓመት ንግሥና ላይ ነው (ራዕይ 20) ማለትም እነርሱ መጽሐፍ ቅዱሳዊውን አትኩሮት ስተውታል፣ የአብን ዘላለማዊ ንግሥና። የክርስቶስ ንግሥና ቀዳሚ ሁነት ነው። ሁለቱ የክርስቶስ ምጽአቶች በብኪ ግልጽ እንዳይደሉ፣ እንዲሁ ደግሞ የመሲሑ ጊዜያዊ ንግሥና!

የኢየሱስ ስብከትና ትምህርት ቁልፉ የእግዚአብሔር መንግሥት ነው። እሱም ሁለቱንም ነው፣ የአሁን (በመዳንና በአገልግሎት)፣ እና የወደፊቱ (በመስፋፋትና በኃይል)። ራዕይ፣ እሱም በመሲሐዊ የሺህ ዓመት ንግሥና ላይ የሚያተኩር ከሆነ (ራዕይ 20)፣ ቀዳሚ ሁነት ነው፣

የመዳረሻ ሳይሆን (ራዕይ 21-22)። ከብኪ አኳያ ግልጽ አይደለም፣ ጊዜያዊ ንግሥና ስለማስፈለጉ፤ እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የዳንኤል 7 መሲሐዊ ንግሥና ዘላለማዊ ነው፣ የሺህ ዓመት ሳይሆን።

**ስድስተኛ ተቃርኖ** (የክርስቶስ በቶሎ መመለስ አልያም የሚዘገይ ዳግም ምጽአት)

አብዛኞቹ አማኞች ያስቡ የነበሩት ኢየሱስ በቶሎ፣ በድንገት፣ እና ሳይታሰብ እንደሚመጣ ነበር (ማቴ. 10:23; 24:27,34,44; ማርቆስ 9:1; 13:30; ራዕ. 1:1,3; 2:16; 3:11; 22:7,10,12,20)። ነገር ግን እያንዳንዱ ጠባቂ የአማኝ ትውልድ እስካሁን ድረስ ተሳስቷል! ቶሎነቱ (የወዲያው) የኢየሱስ መምጣት የእያንዳንዱ ትውልድ ብርቱ ቃል ኪዳናዊ ተስፋ ነው፣ ነገር ግን እውነታው ለአንደኛው ብቻ ነው (እናም ለአንዱ ለሚሳደደው)። አማኞች መኖር የሚኖርባቸው እሱ ነገ እንደሚመጣ ነው፣ ነገር ግን ታላቁን ተልዕኮ ማቀድና መተግበር ይኖርባቸዋል (ማቴ. 28፡ 19-20) ቢዘገይም።

ወንጌላት ላይ አንዳንድ ምንባቦች (ማርቆስ 13:10; ሉቃስ 17:2; 18:8) እና 1 እና 2 ተሰሎንቄ የተመሠረቱት በዳግም ምጽአቱ መዘግየት ላይ ነው (ምጽአት)። ቀድመው መሆን ያለባቸው ታሪካዊ ሁነቶች ይኖራሉ፡

1. ዓለም አቀፍ የወንጌል ስርጭት (ማቴ. 24:14; ማርቆስ" 13:10)
2. "የኃጢአት ሰው" መገለጥ (ማቴ. 24:15; 2 ተሰሎንቄ 2; ራዕይ 13)
3. ታላቁ መከራ (ማቴ. 24:21,24; ራዕይ 13)

ሆን ተብሎ የተደረገ አሻሚነት አለ (ማቴ. 24:42-51; ማርቆስ 13:32-36)! በየቀኑ የመጨረሻህ እንደሆነ እያሰብክ ኑር፣ ነገር ግን ለወደፊቱ አገልግሎት እያቀድክና እየተዘጋጀህ!

**ኀብራዊ ወጥነት እና ሚዛናዊነት**

መባል የሚኖርበት የተለያዩ የዘመናዊ የፍጻሜ ዘመን ጽንሰ-ሐሳብ ተርጓሚዎች አስተምህሮ ሁሉ ግማሽ እውነት እንደያዘ ነው። እነርሱ አንዳንዶቹን ጽሑፎች ደኅና አድርገው ያብራሯቸዋል፣ ይተረጉሟቸዋልም። ችግሩ የሚያርፈው ኀብራዊ ወጥነት እና ሚዛናዊነት ላይ ነው። ዘወትር የቅድመ-ግምት ቅንብር ይኖራል፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጽሑፍን የሚጠቀም፣ ቅድመ-ቅንብር ሥነ-መለኮታዊ መዋቅርን ለመሙላት። መጽሐፍ ቅዱስ ሎጂካዊ፣ ዜና መዋዕላዊ፣ ስልታዊ የፍጻሜ ዘመን ሥነ-መለኮት የለውም። እሱ እንደ ቤተሰብ ፎቶ መያዣ ነው። ፎቶዎቹ እውነት ናቸው፣ ነገር ግን ዘወትር በሥርዓት፣ በይዘት፣ በሎጂካዊ ቅደም ተከተል አይደሉም። አንዳንዶቹ ፎቶዎች ከፎቶ መያዣው ላይ ወድቀዋል እናም የኋለኛው ትውልድ የቤተሰብ አባላት እንዴት መልሰው እንደሚያስቀምጧቸው በትክክል አያውቁም። ራዕይን በአግባቡ ለመተርጎም ቁልፉ የዋነኛው ደራሲ ሐሳብ ነው፣ በጽሑፋዊ ዘውጉ ምርጫ ላይ የተገለጠው። አብዛኞቹ ተርጓሚዎች የራሳቸውን የትርጓሜ መሣሪያዎች እና አገባቦች መጠቀም ይሻሉ፣ ከሌሎች የአኪ ዘውጎች፣ ወደ ራሳቸው የራዕይ ትርጓሜ። እነርሱም ብኪ ላይ ያተኩራሉ፣ የኢየሱስና የጳውሎስ ትምህርቶች ሥነ-መለኮታዊ መዋቅሩን እንዲያቀናብሩ ከማድረግ ይልቅና ራዕይ እንዲያብራራ ከማድረግ።

መቀበል የሚኖርብኝ፣ ይሄንን ሐተታ ራዕይ ላይ የማደርገው በፍርሃትና በመጠንቀቅ ነው፣ በራዕ. 22፡18-19 ላይ ካለው ርግማን ሳይሆን፣ ነገር ግን በዚህ መጽሐፍ ትርጓሜ ላይ ካለው የተቃርኖ ደረጃ ሳቢያ፣ እንዲሁም በእግዚአብሔር ሕዝብ መካከል እየቀጠለ ባለው። የእግዚአብሔርን ራዕይ እወዳለሁ። እሱ እውነት ነው፣ ሰዎች ሁሉ ሐሰተኛ ሲሆኑ (ሮሜ. 3፡4)! እባካችሁን ይሄንን ሐተታ እንደ ሐሳብ ማነሣሻ ሙከራ ተጠቀሙበት፣ እንደ ውሳኔያዊ ሳይሆን፣ እንደ ምልክት ሰሌዳ እንጂ፣ እንደ መንገድ ካርታ ሳይሆን፣ እንደ "ቢሆንስ፣" እንጂ፣ እንደ "ጌታ እንዲህ ብሏል" ሳይሆን። እኔ ፊት ለፊት ነው የመጣሁት፣ ከነገዛ ራሴ አለመብቃት፣ ፍርደ-ገምድልነት፣ እና ሥነ-መለኮታዊ አጀንዳ ጋር። ሌሎችን ተርጓሚዎችን ተመልክቻለሁ። እሱም ከሞላ ጎደል የሚመስለው ሰዎች ራዕይ ላይ ማግኘት የሚሹትን እንደሚያገኙ ነው። ዘውጉ ያላግባብ ጥቅም ላይ ለመዋል ራሱን የሰጠ ነው! ሆኖም፣ እሱ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ያለው ለዓላማ ነው። የእርሱ እንደ ማጠቃለያ "ቃል" መቀመጥ በአጋጣሚ አይደለም። እሱ ከእግዚአብሔር መልእክት አለው፣ ለልጆቹ፣ በእያንዳንዱና በሁሉም ትውልድ። እግዚአብሔር እንድንገነዘብ ይፈልጋል! እጅ ለእጅ እንያያዝ፣ ሰፈሮችን ከመቆርቆር ይልቅ፤ ግልጽና ማዕከላዊ የሆነውን እናጽና፣ እውነት ሊሆን ይችላል፣ ይሆናል፣ ቢሆንስ የሚለውን ሁሉ ሳይሆን (ትተን)። እግዚአብሔር ሁላችንንም ይርዳን!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

***መዝሙር ፡ 37፡1-6***

**1በክፉዎች ላይ አትቅና፥**
**ዓመፃንም በሚያደርጉ ላይ አትቅና**
**2እንደ ሣር ፈጥነው ይደርቃሉና፥**
**እንደ ለመለመ ቅጠልም ይረግፋሉና።**
**3በእግዚአብሔር ታመን፥ መልካምንም አድርግ፥**
**በምድርም ተቀመጥ፥ ታምነህም ተሰማራ።**
**4በእግዚአብሔር ደስ ይበልህ፥**
**የልብህንም መሻት ይሰጥሃል።**
**5መንገድህን ለእግዚአብሔር አደራ ስጥ፥**
**በእርሱም ታመን፥ እርሱም ያደርግልሃል።**
**6ጽድቅህን እንደ ብርሃን፥-**
**ፍርድህንም እንደ ቀትር ያመጣል።**

**37፡1-6** ይህ አንጓ ሰባት ተተኳሪዎችና ሦስት ተጽዕኖዎች አሉት። እነዚህ ጸሎቶች አይደሉም፣ ነገር ግን ለታማኝ ማስጠንቀቂያዎች እንጂ /ማለትም፣ ምን ለማድረግና ላለማድረግ/።

1. አትቅና – ቢዲቢ 354፣ ኬቢ 351፣ *ሂዝፓል ተጽዕኗዊ፣ ተመሳሳይ መልክ ከቁ. 7፣8 ጋር፤* ምሳ. 24:19 ተመልከት፤ *ቃሉ የሚለው "መቃጠል፣" ወይም "መንደድ" ነው፣ እናም በዘይቤነት ጥቅም ላይ የሚውለውም ለቁጣ ነው፤ እዚህጋ ከ"መቅናት" ጋር ጥንድ ሆኗል፣* (ቢዲቢ 888)
2. አትቅና – ቢዲቢ 888፣ ኬቢ 1109፣ *ፔል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ* መዝ. 73:3፤ ምሳ. 3:31፤ 23:17፤ 24:1፣19

የኃጢአተኛ ሕይወት ስኬተኛና ደስተኛ ይመስላል፣ ነገር ግን ለአጭር ጊዜ የሚቆይ ነው፤ በመዳረሻቸውም የተስፋይቱን ምድር አይወርሱም።

1. እነርሱ እንደ ሣር ፈጥነው ይደርቃሉ – ቢዲቢ 576፣ ኬቢ 593፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ፣* ኢዮብ 14:2፤ መዝ. 90:5-6፤ 103:15-16፤ ኢሳ. 40:6-8
2. እነርሱ እንደ ለመለመ ቅጠል ፈጥነው ይረግፋሉና – ቢዲቢ 615፣ ኬቢ 663፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*

እምነት በሌላቸው የአጭር ጊዜ ስኬት አንጻር፣ የታመኑት ተከታዮች ማድረግ የሚኖርባቸው፣ (37:3-5፣ 7 /ሰባት/ ተተኳሪዎች አሏቸው)

1. በያህዌ *መታመን* – ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል ተተኳሪ፣* ዝኪ. ቁ. 3፣5፤ መዝ. 52:8፤ 62:8፤ መዝ. 3:5-6
2. *መልካምን ማድረግ* – ቢዲቢ 793፣ ኬቢ 889፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. በምድር *መኖር* – ቢዲቢ 1014፣ ኬቢ 1496፣ *ቃል ተተኳሪ*
4. *ታማኝነትን ማሳደግ* – ቢዲቢ 944፣ ኬቢ 1258፣ *ቃል ተተኳሪ*
5. በያህዌ ደስ *መሰኘት* – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ *ሂዝፔል ተተኳሪ* (ማለትም፣ በሥጋዊ ብልጽግና ሳይሆን)
6. *መንገድህን አደራ ስጥ* (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:2 ላይ) ለያህዌ – ቢዲቢ 164፣ ኬቢ 193፣ *ቃል ተተኳሪ*
7. በእርሱ *ታመን* – ቢዲቢ ከቁ. 1 ጋር ተመሳሳይ

*ያህዌ ያደርጋል*

1. ይሰጣል (ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) ለታማኝ ተከታይ "የልብህን *መሻት*፣" ቁ. 4
2. "እሱም ያደርገዋል" (ቢዲቢ 793፣ ኬቢ 889፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*)፣ ቁ. 5
3. እሱም ጽድቅህን እንደ ብርሃን ያወጣል
4. እሱም ፍርድህን እንደ ቀትር ያወጣል /ቁ. 3 እና ቁ. 4 ትይዩ ናቸው የሚያመለክቱትም የፍርድ ቤትን ጉዳይ ነው ወይም የመጨረሻው ዘመንን ዘይቤአዊ ፍርድ/

**37፡4ለ** ይህ ዓይነቱ የቅኔ ስንኝ ለእኔ በግል ዘወትር ብዙ የሚለው አለ፣ ነገር ግን እኔ እሱን በትክክል ለመተርጎሜ ርግጠኛ አይደለሁም። እኔ ይሄንን ዘወትር የምጠቀመው ለማስረገጥ ነው፣ እኛ *ታማኝ* ተከታዮች ከሆንን ትክክለኛውን ነገር እንደምንሻ ነው፣ ያህዌ ለልባችን ስለነገረን (ኤር. 31:31-34፤ ሕዝ. 36:26-27)። ነገር ግን በርግጥ የሚያመለክተው የታማኝ ተከታይን የተመለሰ ጸሎት ነው (መዝ. 20:4-5፤ 21:2፤ 145:19፤ ማቴ. 7:7-8)። *ሥነ-መለኮታዊው* ጉዳይ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰዎች ነጻ ፍቃድ መካከል ያለ መስተጋብር ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 25:12 ላይ፤ ኒዶቲ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 444)። አንዳንዴ በጥንቃቄ የተሠራ ትርጓሜ መልካም ስብከትን ያስገኛል!

***መዝሙር ፡*** **37፡7-11**

**7 ለእግዚአብሔር ተገዛ ተስፋም አድርገው።**
***መንገድም በቀናችለትና ጥመትን በሚያደርግ ሰው አትቅና።***
**8 ከቍጣ *ራቅ መዓትንም* ተው**
**እንዳትበድል አትቅና።**
**9 ክፉ አድራጊዎች ይጠፋሉና**
**እግዚአብሔርን ተስፋ የሚያደርጉ ግን እነርሱ ምድርን ይወርሳሉ።**
**10 *ገና ጥቂት፥ ኃጢአተኛም* አይኖርም**
**ትፈልገዋለህ ቦታውንም አታገኝም።**
**11 *ገሮች ግን ምድርን* ይወርሳሉ፥**
**በብዙም ሰላም ደስ ይላቸዋል።**

**37፡7-11** ይህ የቀዳሚው አንጓ ቀጣይ ነው።

1. ለታማኝ ማስጠንቀቂያ
   ሀ. በእግዚአብሔር *ዕረፍ* – ቢዲቢ 198፣ ኬቢ 226፣ *ቃል ተተኳሪ*
   ለ. እሱን በትዕግሥት ጠብቅ – ቢዲቢ 296፣ ኬቢ 297፣ *ሂዝፖለል ተተኳሪ* (ማለትም፣ ያህዌ በጊዜያዊነትም ሆነ በፍጻሜ እንዲሠራ)
   ሐ. አትቅና – ከ37:1 ጋር ተመሳሳይ
   መ. ከቁጣ *ራቅ* – ቢዲቢ 951፣ ኬቢ 1276፣ *ሂፊል ተተኳሪ* (ማለትም፣ በራስህ ለመበቀል አትሞክር)
   ሠ. መዓትንም ተው – ቢዲቢ 736፣ ኬቢ 806፣ *ቃል ተተኳሪ*
   ረ. አትቅና – ከ37:1፣7 ጋር ተመሳሳይ
2. የእምነተ-ቢስ ዕጣ-ፈንታ ርግጠኛ ከመሆኑ የተነሣ
   ሀ. የእርሱ ብልጥግና ይቆረጣል /ማለትም፣ ሞት/
   ለ. ክፉ ምንም ስፍራ አይኖረውም /እንደ በረሀ አበባዎች፣ ሳይታሰብ/
3. ስለዚህ፣ የታመነው /ማለትም፣ ያህዌን በትዕግሥት የሚጠብቁት፣ ቁ. 9ለ/
   ሀ. ምድርን ይወርሳሉ፣ ዝኪ. 37:9፣11፣22፣29፣34፣ መ ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፣ ጽሑፋዊ ይዘት ላይ፤ እና ልዩ ርዕስ መዝ. 1:2/
   ለ. በተትረፈረፈ ብልጽግና ይደሰታሉ

**37:7 "በትዕግሥት ጠብቅ"** ኤምቲ ግሥ አለው (ቢዲቢ 296 I፣ ኬቢ 297)፣ በጥሬው "መሾር፣" "መዝለል፣" "መጠማዘዝ" (ማለትም፣ በሥቃይ ጊዜ)። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው "መጠበቅ" በሚለው መልኩ ነው ኢዮብ 35:14 ላይ (ፖለል)። እዚህጋ ብቻ ነው መዝ. 37:7 ላይ (ሂዝፖለል) "በትዕግሥት መጠበቅ" የሚለው። ከዚህ የተነሣ አእት መጽሐፍ ቅዱስ (ዝኪ. ገጽ 895፣ ቁ. 9) ማስተካያ ሰንዝሯል፣ ለተለየ የዕብራይስጥ ሥር (ማለትም፣ ከ ኀየ ወደ ኀከ ፣ ቢዲቢ 403፣ ሂፊል)።

**37:8** እዚህም እንደገና ተደጋጋሚው የብኪ አጽንዖት አለ፣ የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና ቅድመ-አዋቂነት ዝኪ. /37:23/። ታሪክ ሁሉ በፊቱ አለ። ታማኝ ተከታዮች ይታመናሉ

1. ያለፈው ይቅር መባሉን
2. የአሁኑ ኃይል መታጠቁን
3. የወደፊቱ ደኅንነት መጠበቁን

**37:10 "ገና ጥቂት ጊዜ"** ይህ የዕብራይስጥ ምናብ ነው ቀድመው ለተወሰኑ ክስተቶች። ያህዌ ጊዜያትን ይቆጣጠራል። ዕቅድ፣ ዓላማ፣ እና ትክክለኛ ውጤት አለ። ጽድቅ በመጨረሻ ድል አድራጊ ይሆናል፣ እናም ኃጢአተኝነት ይጋለጣል፣ ይፈረድበታል፣ ይጠፋል /ዝኪ. 37:13/!

**37:11 "ገሮች ምድርን ይወርሳሉ"** ይህ በኢየሱስ ተጠቅሷል፣ በተራራው ስብከት ማቴ. 5:5 (LXX)፣ እዚያም "መሬት" ወደ "ምድር" የተቀየረበት /ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት/።

**መዝሙር ፡ 37:12-15**

**[12]ኃጢአተኛ ጻድቁን ይመለካከተዋል፥**
**ጥርሱንም በእርሱ ላይ ያንገጫግጫል።**
**[13]እግዚአብሔር ይሥቅበታል፥**
**ቀኑ እንደሚደርስ አይቶአልና።**
**[14]ኃጢአተኞች ሰይፋቸውን መዘዙ፥**
**ቀስታቸውንም ገተሩ ድህውንና ችግረኛውን ይጥሉ ዘንድ**
**ልበ ቅኖችንም ይወጉ ዘንድ**
**[15]ሰይፋቸው ወደ ልባቸው ይግባ፥**
**ቀስታቸውም ይሰበር።**

**37:12-15** የኃጢአተኛ ድርጊቶች በታማኝ ላይ እና የያህዌ ምላሽ።

1. ኃጢአተኛ
   ሀ. በጻድቅ ላይ የተሸረበ ሴራ
   ለ. ያንገጫግጫሉ /ጥርሳቸውን/ በእርሱ/በእነርሱ ላይ፣ ኢዮብ 16:9፤ መዝ. 35:11፤ ሰቆ. 2:16፤ ሐዋ. 7:54
   ሐ. ሰይፋቸውን መዘዙ
   መ. ቀስታቸውን ገተሩ
      (1) ደህውን ይጥሉ ዘንድ
      (2) ችግረኛውን ይጥሉ ዘንድ
      (3) ቅኖችን ይወጉ ዘንድ
2. የያህዌ ምላሽ
   ሀ. ይስቅበታል/ይስቅባቸዋል፣ መዝ. 2:4፤ 59:9
   ለ. ቀኑ/ቀናቸው /ማለትም፣ ፍርዳቸው/ መድረሱን አውቋልና፣ ሁለቱም፣ ጊዜያዊም ሆነ ፍጻሜያዊ
   ሐ. ሰይፋቸው ይሰበራል /በያህዌ የተገለበጠ/
   መ. ቀስታቸው ይሰበራል /በያህዌ የተገለበጠ/

**መዝሙር ፡ 37:16-22**

**[16]ለጻድቅ ያለው ጥቂት**
**ከብዙ ከኃጢአተኞች ሀብት ይበልጣል።**
**[17]የኃጥአን ክንድ ትሰበራለችና**
**እግዚአብሔር ግን ጻድቃንን ይደግፋቸዋል።**
**[18]የንጹሓንን መንገድ እግዚአብሔር ያውቃል፥**
**ርስታቸውም ለዘላለም ነው**
**[19]በክፉ ዘመንም አያፍሩም**
**በራብ ዘመንም ይጠግባሉ።**
**[20]ኀጥአን ግን ይጠፋሉ፥**
**የእግዚአብሔር ጠላቶች በከበሩና ከፍ ከፍ ባሉ ጊዜ**
**እንደ ጢስ ይጠፋሉ።**
**[21]ኃጢአተኛ ይበደራል አይከፍልምም**

ጻድቅ ግን ይራራል ይሰጣልም።
[22]እርሱን የሚባርኩት ምድርን ይወርሳሉና
የሚረግሙት ግን ይጠፋሉ።

**37፡16-22** ይህ አንጓ ተለጣጣቂ ተቃርኖ ነው /ተቃርኗዊ ትይዩነት/።

1. ቁጥር 16
   ሀ. በጻድቅ ያለ ጥቂት ይሻላል (ምሳ. 15:16-17፤ 16:8፤ 28:6፤ ይህ ሥነ-መለኮታዊ ሚዛን ነው፣ የ 37፡25/
   ለ. በኃጢአተኛ ካለ ብዙ /ማለትም፣ በኃጢአተኛ ብልጽግና አትቅና፣ 37፡1-2/
2. ቁጥር 17
   ሀ. የከፋዎች ክንድ ይሰበራል
   ለ. ያህዌ ጻድቅን ይደግፋል
3. ቁጥር 18-20
   ሀ. ንጹሐን፣ ቁ. 18-19
      (1) ያህዌ ቀናቸውን ያውቃል
      (2) ርስታቸው ለዘላለም ነው
      (3) በክፉ ዘመንም አያፍሩም
      (4) በራብ ዘመን ይጠግባሉ
   ለ. ኃጢአተኞች
      (1) ይጠፋሉ
      (2) ይጠፋሉ /ኤምቲ ርግጠኝነት የለውም፣ ዐውደ-ጽሑፍ ይገልጸዋል፣ እንደ ጺደይ አበባ፣ ዝከ. ቁ. 2/
4. ቁጥር 21
   ሀ. ኃጢአተኛ ይበደራል አይከፍልምም
   ለ. ጻድቅ ግን ይራራል ይሰጣልም
5. ቁጥር 22
   ሀ. በያህዌ የተባረኩ ምድርን ይወርሳሉ
   ለ. በያህዌ የተረገሙ ይጠፋሉ

## *መዝሙር ፡ 37፡23-26*

[23]የሰው አካሄድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ይጸናል፥
መንገዱንም ይወድዳል።
[24]ቢወድቅም ለድንጋፄ አይጣልም፥
እግዚአብሔር እጁን ይዞ ይደግፈዋልና።
[25]ጐለመስሁ አረጀሁም
ጻድቅ ሲጣል፥
ዘሩም እህል ሲለምን አላየሁም።
[26]ሁልጊዜ ይራራል ያበድርማል፥
ዘሩም በበረከት ይኖራል።

**37፡23-26** ይህ አንጓ የሚገልጸው ታማኝ ተከታይ/ዮችን/ ነው።

1. የእርሱ/እርሷ አካሄድ በያህዌ የጸና ነው
2. ያህዌ በእርሱ/በእርሷ መንገድ ደስ ይለዋል
3. እርሱ/እርሷ በሚወድቁ ጊዜ
   ሀ. ለድንጋጤ አይጣሉም /ማለትም፣ የጥፋት ዘይቤ/
   ለ. ያህዌ የእርሱን/እርሷን እጅ ስለሚይዝ /ቅዱሳን ከጊዜ ወደ ጊዜ ሊደክሙ ይችላሉ፣ ያህዌ ግን አይደለም/
4. መዝሙረኛው /በሕይወት ልምድ ተሞክሮ/ ጻድቅ ሲጣል ፈጽሞ አይቶ አያውቅም
5. መዝሙረኛው ዘራቸው እህል ሲለምን አይቶ አያውቅም
6. እሱ/እሷ ይለግሳል ያበድራልም
7. የእርሱ/እርሷ ዘራቸው ይባረካል

**37፡25** ይህ የአይሁድ አስተሳሰብ ነው፣ በሙሴ ኪዳን ላይ በመመርኮዝ /ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30/። ይህ ማለት ዛሬ ይተረጎማል ማለት አይደለም፣ ድሆችና ችግረኞች ሁሉ አማኞች ሊሆኑ እንደማይችሉ፡ ኪዳናቱ ተለውጠዋል፣ ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት መ ተመልከት። አጠር ላለ የተሻለ ማብራሪያ፣ ለዚህ ቁጥር፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ጠንካራ አባባሎች ተመልከት፣* ገጽ 267-268።

## *መዝሙር ፡ 37፡27-34*

[27]ከክፉ ሽሽ፥ መልካምንም አድርግ
ለዘላለምም ትኖራለህ።

**[28]እግዚአብሔር ፍርዱን ይወድዳልና፥**
**ቅዱሳኑንም አይጥላቸውምና**
**ለዘላለምም ይጠብቃቸዋል**
**ለንጹሓንም ይበቀልላቸዋል የኀጥኣን ዘር ግን ይጠፋል።**
**[29]ጻድቃን ምድርን ይወርሳሉ፥**
**በእርስዋም ለዘላለም ይኖራሉ።**
**[30]የጻድቅ አፍ ጥበብን ያስተምራል፥**
**አንደበቱም ፍርድን ይናገራል።**
**[31]የአምላኩ ሕግ በልቡ ውስጥ ነው፥**
**በእርምጃውም አይሰናከልም።**
**[32]ኃጢአተኛ ጻድቁን ይመለከተዋል፥**
**ሊገድለውም ይወድዳል።**
**[33]እግዚአብሔር ግን በእጁ አይተወውም፥**
**በተፋረደውም ጊዜ አያሸንፈውም።**
**[34]እግዚአብሔርን ደጅ ጥና፥**
**መንገዱንም ጠብቅ፥ ምድርንም ትወርስ ዘንድ**
**ከፍ ከፍ ያደርግሃል ኃጢአተኞችም ሲጠፉ ታያለህ።**

**37፡27-34** ይህ አንጓ፣ እንደ ቁ. 1-6 በርካታ ተተኳሪዎች አሉት /6/ *ታማኝን* የሚያስጠነቅቁ። ይህም ሌለኛው አንጓ ነው፣ የታማኝ ተከታዮችን ድርጊቶች የሚገልጹ።

1. *ማስጠንቀቂያዎች /ማለትም፣ ተተኳሪዎች/*
   ሀ. ከክፉ ራቅ፣ ቁ. 27 – ቢ.ዲ.ቢ. 693፣ ኬ.ቢ. 747፣ *ቃል ተተኳሪ*
   ለ. መልካምን አድርግ፣ v. 27 – ቢ.ዲ.ቢ. 793፣ ኬ.ቢ. 889፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ ዝኪ. 37:3
   ሐ. ለዘላለም ይኖራል፣ ቁ. 27 – ቢ.ዲ.ቢ. 1014፣ ኬ.ቢ. 1496፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ ዝኪ. 37፡18፣29
   መ. ያህዌን መጠበቅ፣ ቁ. 34 – ቢ.ዲ.ቢ. 875፣ ኬ.ቢ. 1082፣ *ፔል ተተኳሪ*፣ ዝኪ. 37:9
   ሠ. መንገዱን መጠበቅ፣ ቁ. 34 – ቢ.ዲ.ቢ. 1036፣ ኬ.ቢ. 1581፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. የማስጠንቀቂያዎቹ ምክንያቶች
   ሀ. ያህዌ ፍትሕን ይወዳል
   ለ. ያህዌ የእርሱ የሆኑትን አይተውም
   ሐ. እነርሱም ለዘላም ይጠበቃሉ
   መ. እነርሱ ምድርን ይወርሳሉ
   ሠ. በምድሩም ላይ ለዘላም ይኖራሉ
   ረ. እነርሱ ጥበብን/ፍትሕን ይናገራሉ
   ሰ. እነርሱ/እሱ የእግዚአብሔር ሕግ አላቸው በልባቸው/በልቡ
   ሸ. እግሩ አይሰናከልም
   ቀ. ያህዌ አይተወውም/አይተዋቸውም
   በ. እሱ/እነርሱ በፍርድ አይኮነኑም

የኪዳን አማኝ መሆን የአንዱን የሕይወት፣ የሐሳብ፣ እና ተስፋ ገጽታ ይቀይረዋል። ፍጹም የሆነ ልዩነት አለ በአማኝ ተከታይ እና በእምነተ-ቢስ ሰው መካከል። እምነተ-ቢስ ሊሆን የሚችለው

1. ጣዖት አምላኪ
2. የማይታዘዝ የኪዳን ሰው
3. ተግባራዊ አምላክ-የለሽ
4. ስልቹ ተከታይ
5. ክፉ ባለጠጋ ሰው
6. የማይታመን የፖለቲካ ሰው

ቁጥር 32 ላይ እሱ/እሷ የተገለጹት እንደ /አንጓ 35-40 ተመልከት/

1. ጻድቅን ይሰልላል
2. እርሱን/እነሱን ሊገድል ይፈልጋል

**37፡28 "ለዘላለም ይጠብቃቸዋል"** LXX ይሄንን ይቀይረዋል ወደ "ክፉ አድራጊዎች ይሳደዳሉ።" ይህ የሚገልጸው መስቀልያውን አወቃቀር ለመጠበቅ ነው (ማለትም፣ አይን) እናም ከትይዩው ጋር ይገጥማል። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ለኤምቲ "ለ" ለደረጃ ይሰጠዋል /መጠነኛ ጥርጣሬ/።

1. ኤምቲ – נשמרו
2. LXX – נשדו (አእመቅ፣ አኢመቅ፣ የተእመቅ)

**37፡31 "የእግዚአብሔር ሕግ"** ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 435) ከበርካታ ቃላት አንደኛው ነው፣ ያህዌ ለእስራኤል ያደረገውን መገለጽ ጥቅም ላይ የዋለ /ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ 1፡2/።

▣ **"በልቡ"** ይህ የያህዌን መገለጥ ውስጣዊ ማድረግ ነው /ማለትም፣ የእግዚአብሔር ሕግ በልብ የተጻፈ/ እና "የአዲስ ኪዳን" ምልክት፣ የኤር 31፡ 31-34።

▣ **"ርምጃውም አይሰናከልም"** መልካም አኗኗር በዘይቤነት የተገለጸው እንደ ቅን፣ የተስተካከለ፣ ማሰናከያ እንደሌለበት መንገድ ነው፣ ግልጽ የሆነ መንገድ /ዝኪ. ቁ. 34ሀ፣ "መንገዱ" ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 1፡1 ላይ/። ተቃራኒው ሊሆን የሚችለው

1. ርምጃው ይሰናከላል
2. የሚያዳልጥ ጭቃ
3. የሚያሰናክል

በአኪ. ይኸው ተመሳሳይ ምናባዊ ምስያ ይገኛል (ማለትም፣ "መራመድ፣" ኤፌ. 4:1፣17፤ 5:2፣15)።

**መዝሙር ፡ 37፡35-40**

**35ኃጥአን ከፍ ከፍ ብሎ**
**እንደ ሊባኖስ ዝግባም ለምልሞ አየሁት።**
**36ብመለስ ግን አጣሁት ፈለግሁት**
**ቦታውንም አላገኘሁም።**
**37ቅንነትን ጠብቅ፥ ጽድቅንም እይ**
**ለሰላም ሰው ቅሬታ አለውና።**
**38በደለኞች በአንድነት ይጠፋሉ።**
**የኃጢአተኞች ቅሬታ ይጠፋል።**
**39የጻድቃን መድኃኒታቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው**
**በመከራቸውም ጊዜ መጠጊያቸው እርሱ ነው።**
**40እግዚአብሔር ይረዳቸዋል፥ ያድናቸዋልም፥**
**ከኃጢአተኞችም እጅ ያወጣቸዋል፥ ያድናቸዋል፥**
**በእርሱ ታምነዋልና።**

**37፡37-40** ይህ አንጓ በጻድቅ እና በኃጢአተኛ መካከል ያለውን ተቃርኖ ያጠቃልላል።

1. ኃጢአተኛ
   ሀ. ሞገደኛ /"በሽብር የሚያውክ፣" ቢዲቢ 792/
   ለ. ያንሰራፋል /በፍጥነት፣ ቢዲቢ 947/ ተጽዕኗዊ ኃይሉ እና ስፍነቱ እንደ ተመቸው ዛፍ በምድሪቱ ላይ /ኤምቲ ርግጠኝነት የለውም/
   ሐ. ዘመኖቹ ተወስነዋል፣ ከዛም ምንም ያህል አይኖርም
   መ. እሱ/እነርሱ ከዝርያቸው ጋር ይጠፋሉ /ከታች ቁ. 2ሐ ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት/
2. ጻድቅ
   ሀ. ይመለከታል /"ይጠብቃል"/ ጻድቅ ሰው /ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 18፡20-24/ – ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ *ቃል ተተኳሪ*
   ለ. እነሆ ጻድቁ – ቢዲቢ 90፣ ኬቢ 1157፣ *ቃል ተተኳሪ*
   ሐ. የሰላም ሰው ዝርያ ይኖረዋል /ከሕይወት በኋላም ሆነ ልጆች/
   መ. በያህዌ ድነዋል
   ሠ. ያህዌ ኃይላቸው ነው በችግር ጊዜ
   ረ. ያህዌ ይረዳቸዋል
   ሰ. ያህዌ ይታደጋቸዋል

ይሄ ሁሉ የሚከሰተው በእርሱ ስለሚታመኑ ነው

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ከመዝሙር 49 እና 73፣ እና ከመጽሐፈ ኢዮብ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
2. ሰዎች እንደ ሣርና አበባ ለምን ተገለጹ?
3. "መታመን" የሚለው ቃል ሥርወ-ቃል ምንድነው እና ለሕይወታችን ያለው ጠቀሜታ ምንድነው?
4. የዚህ መዝሙር ማዕከላዊ ጭብጥ ምንድነው?
5. ቁጥር 16 እና 24 ይሄን ያህል ጠቃሚ ማመዛዘኛ የሆኑት ለምንድነው፣ ለባህላዊው የብኪ ጥበብ?
6. ይህ መዝሙር ስለ ጊዜያዊው ወይስ የፍጻሜያዊው ፍርድ ያስተምራልን? ለምን?

## መዝሙር 38
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ንስሐ የሚገባ መከረኛ ጸሎት ኤምቲ መግቢያ "የዳዊት መዝሙር ለመታሰቢያ" | በተግሣጽ ጊዜ ጸሎት | የፈውስ ጸሎት በሕመም ጊዜ (ሰቆቃ) | መከራ ለሚቀበል ጸሎት | በመከራ ጊዜ ጸሎት |
| 38:1-8 | | | | |
| | 38:1-2 | 38:1-2 | 38:1-2 | 38:1-3 |
| | 38:3-5 | 38:3-4 | 38:3-4 | |
| | | | | 38:4-6 |
| | | 38:5-6 | 38:5-8 | |
| | 38:6-8 | | | |
| 38:9-12 | | | | |
| | | 38:7-8 | | 38:7-8 |
| | 38:9-10 | 38:9-11 | 38:9-12 | 38:9-10 |
| | 38:11-12 | | | 38:11-12 |
| 38:13-22 | | | | |
| | | 38:12 | | |
| | 38:13-14 | 38:13-14 | 38:13-14 | 38:13-14 |
| | 38:15-20 | 38:15-16 | 38:15-17 | 38:15-16 |
| | | 38:17-20 | | 38:17-18 |
| | | | 38:18-20 | |
| | | | | 38:19-20 |
| | 38:21-22 | 38:21-22 | 38:21-22 | 38:21-22 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር በብዛት የጋራ የሆነ ነገር አለው፣ ከመዝሙር 32 እና 51 ጋር።

ለ. በአይሁድ አስተሳሰብ ኃጢአትና ሕመም ግንኙነት አለው። ኃጢአትን መናዘዝ፣ መልስ የሚያገኝ ጸሎትን ያስገኛል እንዲሁም የአእምሮ፣ የመንፈስ፣ እና የአካል መታደስን።
አንዱ የተጠቀሱትን አካላዊ ችግሮች ሁሉ ሲመለከት፣ ባብዛኛው ባሕርዩ ከሕመም ጋር ይያያዛል። እነርሱ ምናልባት ተምሳሌታዊ ሊሆኑ ይችላሉ (ኢሳ. 1:5-6)። እንደዚያ ከሆነ፣ የመዝሙሩ ትኩረት ሥጋዊ ፈውስ አይደለም፣ የኃጢአት ይቅርታ እንጂ!

ሐ. በብዙዎቹ መዝሙራት እንደሆነው፣ ግንኙነቱ

1. *ሥጋዊ ችግሮች*
2. የጠላቶች ጥቃት
3. የባልንጀሮች መተው

*መካካል ያለ ለመሆኑ ርግጠኝነት የለም። እነርሱ ሁሉ ይያያዛሉ፣ እንዴት እንደሆነ ግን ምሥጢር ነው። እነርሱ ጥሬአዊ ወይስ ተምሳሌታዊ ያቸውን፣ ለኃጢአት ማኅበራዊ ውጤቶች?*

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 38፡1-8**

**[1]አቤቱ፥ በቍጣህ አትቅሠፈኝ፥**
**በመዓትህም አትገሥጸኝ።**
**[2]ፍላጾችህ ወግተውኛልና፥**
**እጅህንም አከብደህብኛልና።**
**[3]ከቍጣህ የተነሣ ለሥጋዬ ጤና የለውም ከኃጢአቴም የተነሣ**
**ለአጥንቶቼ ሰላም የላቸውም።**
**[4]ኃጢአቴ በራሴ ላይ ከፍ ከፍ ብሎአልና፥**
**እንደ ከባድ ሸክምም በላዬ ከብዶአልና።**
**[5]ከስንፍናዬ የተነሣ**
**ቍስሌ ሸተተ በሰበሰም**
**[6]እጅግ ጐስቍልሁ ተዋረድሁም፥**
**ሁልጊዜም በትካዜ እመላለሳለሁ።**
**[7]ነፍሴ ስድብን ተሞልታለችና፥**
**ለሥጋዬም ጤና የላትምና።**
**[8]ታመምሁ እጅግም ተቸገርሁ፥**
**ከልቤ ውዝዋዜም የተነሣ ጮኽሁ።**

**38፡1-8** አብዛኞቹ እንግሊዝኛ ትርጉሞች ይሄንን ክፍል ወደ በርካታ አንጓዎች ከፋፍለውታል። የአንጓ ምድብ የዐውደ-ጽሑፋዊ ጉዳይ አይደለም። እሱ ግምታዊ ነው፣ ተመስጧዊ ሳይሆን።

መዝሙረኛው ያለበትን ሁኔታና ስሜት ይገልጻል።

1. የያህዌን ደስ አለመሰኘት ተረድቷል
   ሀ. በቁጣህ አትቅሠፈኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 406፣ ኬቢ. 410፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ መዝ. 6:1
   ለ. በመዓትህም አትገሥጸኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 415፣ ኬቢ. 418፣ ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፤ ይህ ግሥ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ኪዳንን ለመጣስ ነው (ሌዋ. 26:18፣28፤ መዝ. 6:1፤ 39:11፤ 94:10፤ 118:18፤ ሆሴ. 10:10)
2. የያህዌ ቅጣት ተሰምቶታል
   ሀ. ፍላጾችህ ወግተውኛልና፣ ዘዳ. 32:23፤ ኢዮብ 6:4፤ መዝ. 7:12-13፤ 45:5
   ለ. እጅህንም አክብደኽብኛልና፣ መዝ. 32:4፤ 39:10 (ተመሳሳይ ግሦች በሁለቱም ስንኞች፣ ግን በተለያዩ መልኮች፣ ቢ.ዲ.ቢ. 639፣ ኬቢ. 692
3. የያህዌ ደስ አለመሰኘት አካላዊ ውጤት (በኃጢአት ምክንያት፣ 38:3ለ፣4፣5ለ)
   ሀ. ጤና የለውም (ቢ.ዲ.ቢ. 1022፣ *ሻሎም*) ለሥጋዬ
   ለ. አጥንቶቼም ጤና የላቸውም
   ሐ. ቁስሌም ("ምልክት፣" ቢ.ዲ.ቢ. 289) ሸተተ (ቢ.ዲ.ቢ. 92፣ ኬቢ. 107፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ) በሰበሰም (ቢ.ዲ.ቢ. 596፣ ኬቢ. 583፣ *ቃል* የተጠናቀቀ)
   መ. ጎሰቆልኩ ("መጉበጥ" ቢ.ዲ.ቢ. 730፣ ኬቢ. 796፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ፤ "መዋረድ፣" ቢ.ዲ.ቢ. 1005፣ ኬቢ. 1458፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 35:14) በኀዘን
   ሠ. ሆዴ ተሞልታለችና (ቢ.ዲ.ቢ. 569፣ ኬቢ. 583፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) ብግነትን
   ረ. ሀ ላይ የተደገመ
   ሰ. ታመምሁ (ቢ.ዲ.ቢ. 806፣ ኬቢ. 916፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ፣ "ደከምሁ")
   ሸ. ተቸገርሁ (ቢ.ዲ.ቢ. 194፣ ኬቢ. 221፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ፣ *ፔል* መዝ. 51:8)
   ቀ. ጮኽኩ (ቢ.ዲ.ቢ. 980፣ ኬቢ. 1367፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ማለትም የእንስሳ ድምጽ)

የተጠናቀቁትን ጊዜያት ግሦች ድርደራ ተገንዘብ። የያህዌ "ቁጣ" (ቢ.ዲ.ቢ. 893) እና "መዓት" (ቢ.ዲ.ቢ. 409) (ያልተጠናቀቁ) ሆነዋል እናም (የተጠናቀቁ) ሆነው ይቀራሉ! እንዴት ያለው የሚያስፈራ ሁኔታ ነው የሐሳብ እና የሥጋ (38፡4፣ 8ለ)!

**38፡4 "በራሴ ላይ"** ይህ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 716፣ ኬቢ. 778፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) ለውኃ ነው ጥቅም ላይ የዋለው።

1. ጎርፍ እንደ ጦርነት – ኢሳ. 8:8፤ 23:10፤ ዳን. 11:10፣40፤ ናሆም 1:8
2. ሞገድ – በጥሬው ኢሳ. 54:9
3. ሞገድ – የችግሮችና የስሜቶች ዘይቤ – መዝ. 42:8፤ 88:16-17፤ 124:4-5

የመዝሙረኛው በደል በኃጢአት ምክንያት ሸፍኖታል!

**38፡5 "በሰበሰ"** ይህ *ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 596፣ ኬ.ቢ. 628፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ) ሌዋውያን 26 ጥቅም ላይ የዋለ፣ የርግማንና የባርኮት አንቀጽ፣ ዘዳ. 27-28 ላይ ትይዩ የሆነው። እሱም "የሸተተና የበሰበሰ" ብሎ ይገልጸዋል። (ሌዋ. 26:39 [ሁለቴ])። ኃጢአት ያጠፋል! ዘወትር ባስፈሪ መንገዶች!

**38፡6 "ትካዜ"** ይህ ቃል ከዕብራይስጥ *ሥር* ነው፣ "መጨለም" (ቢ.ዲ.ቢ. 871)። እሱም ሊሆን የሚችለው

1. ጥቁር ልብስ መልበስ፣ ለኀዘን ምልክት
2. አቧራ ራስ ላይ ማኖር እና መልበስ፣ ለኀዘን ምልክት
3. ለልብ፣ ነፍስ፣ ሐሳብ ሁኔታ ፈሊጥ (እዚህ በታወቀ ኃጢአት ምክንያት)

▣ **"እጅግ ጐሰቈልሁ ተዋረድሁም"** ሁለት ትይዩ ግሦች አሉ።

1. *መዋረድ* – ቢ.ዲ.ቢ. 730፣ ኬ.ቢ. 796፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ እሱም ሊታይ የሚችለው እንደ፣
   *ሀ. መምታታት* – ኢሳ. 21:3
   ለ. የአእምሮ መታወክ – 1 ሳሙ. 20:30፤ ምሳ. 12:8
   ሐ. በጥሬው — እሱም ከትይዩ *ግሥ* ጋር የሚገጥም
2. *መጎስቆል* — ቢ.ዲ.ቢ. 1005፣ ኬ.ቢ. 1458፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ እሱም የጎበጠ አካልን የሚያመላክት፣ እንደ ተዋረደ ልብ ዘይቤ

**38፡7 "ነፍስ"** በርካታ ቃላት አሉ ብኪ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ሙሉውን አካል የሚወክሉ።

1. ነፍስ — ቢ.ዲ.ቢ. 659፣ *ነፍሽ*
2. *መንፈስ* — ቢ.ዲ.ቢ. 924፣ *ሩሕ*
3. ልብ — ቢ.ዲ.ቢ. 524፣ *ለብ*
4. ኵላሊት — ቢ.ዲ.ቢ. 480
5. እዚህ ብቻ፣ ሆድ — ቢ.ዲ.ቢ. 492

ሌሎች በርካቶችም አሉ። ዐውደ-ጽሑፍ ብቻ ነው የሚወስነው፣ ጽንሰ-ሐሳቡ ምን ማለት እንደሆነ። አንደኛው የሰውነት ብልት ሁሉንም አካል ይወክላል።

***መዝሙር ፡ 38፡9-12***

**9 አቤቱ፥ ፈቃዴ ሁሉ በፊትህ ነው፥**
**ጭንቀቴም ከአንተ አይሰወርም።**
**10 ልቤ ደነገጠብኝ፥ ኃይሌም ተወኝ፥**
**የዓይኖቼም ብርሃን ፈዘዘ።**
**11 ወዳጆቼም ባልንጀሮቼም ከቍስሌ ገለል ብለው ቆሙ፥**
**ዘመዶቼም ርቀው ቆሙ።**
**12 ነፍሴንም የሚሹአት በረቱብኝ፥**
**መከራዬንም የሚፈልጉ ከንቱን ተናገሩ፥**
**ሁልጊዜም በሽንገላ ይመክራሉ።**

**38፡9-12** ይህ አንጓ ደግሞ የደራሲውን አስፈሪ ሁኔታ ይገልጻል።

1. የእርሱን ሁኔታ
   ሀ. መሻቱን (ማለትም፣ ጸሎቱን) በያህዌ ፊት (ማለትም፣ ስለ ምሕረት እና ስለ ኅብረት መመለስ)
   ለ. መቃተቱ በያህዌ ፊት ታውቋል፣ መዝ. 31፡10
2. የእርሱ *ሥጋዊ* ሁኔታ
   ሀ. ልቡ ደንግጧል – ቢ.ዲ.ቢ. 695፣ ኬ.ቢ. 749፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ
   ለ. ኃይሉ ደከመ – ቢ.ዲ.ቢ. 736፣ ኬ.ቢ. 806፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
   ሐ. ዓይኑ ፈዘዘ – *ግሥ* የለውም፤ ይህ ዕውርነትን አያመለክትም፣ ነገር ግን ዘይቤ ነው ጤና፣ ደስታ፣ ሰላም ስለማጣት መዝ. 13:3፤ 1 ሳሙ.14:29፤ ዕዝራ 9:8
3. ከሰዋዊ ነገሮች ጋር የተያያዙ ጉዳዮች
   ሀ. ወዳጆች ርቀው ሲቆሙ
   ለ. ርቀው የቆሙ ባልንጀሮች
   ሐ. ርቀው የቆሙ ዘመዶች
   መ. ሞቱን የሚሹ ጠላቶች
      (1) ወጥመድ አኑረዋል
      (2) ጥፋትን ያበጃሉ
      (3) ቀኑን ሁሉ ተንኮል ያስባሉ፤ ግሡ ቢ.ዲ.ቢ. 211፣ ኬ.ቢ. 237፣. "*ሥቃይ.*" ነው፣ መዝሙረኛው "ይሠቃያል" (ቢ.ዲ.ቢ. 980፣ ቁ. 8) ከፉ ግን "ያዘጋጃል" ምሳ. 24:2)።

**38፡11**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጆት** | ***"መቅሠፍት"*** |
| **አየተመት፣ ጄፒኤስኦኤ** | ***"መከራ"*** |
| **አእቅ** | ***"ቍስል"*** |
| **አኢመቅ** | ***"በሽታ"*** |

***የተእመቅ*** ***"ሕመም"***

*ቃሉ* (ቢዲቢ 619) ፍችው "ምት/ቁስል፣" "መቅሠፍት፣" ወይም "ምልክት፣" ማለት ነው።

1. *መቅሠፍት* – ዘፍ. 12:17፤ ዘጸ. 11:1፤ 1 ነገ. 8:37-38፤ 2 ዜና. 6:28-29፤ መዝ. 39:10፤ 91:10
2. ለምጥ (በብኪ መልኩ) – ሌዋውያን 13-14፤ ዘዳ. 24:8
3. ቁስል – ዘዳ. 17:8፤ 21:5፤ ኢሳ. 53:8
4. ቅጣት (ለልጆች) – 2 ሳሙ. 7:14፤ መዝ. 89:33፤ ምሳ. 6:23

አብዛኞቹ ቃላት ብዙ አጠቃቀም አላቸው ወይም ደግሞ የሰዎች ቃላት ሊያውቃቸውና ሊጠቀምባቸው አልቻለ ይሆናል። ተርጓሚ ወደ ዐውደ-ጽሑፍ ሲመጣ እነርሱ ፍቺ ያስፈልጋቸዋል፣ ዋነኛው ደራሲ ሊል ያሰበውን፣ እና በዘመኑ የነበሩት አድማጮች/አንባቢዎች ሊገነዘቡት የሚችል። ይህ ዐውደ-ጽሑፍ ከመለኮት የተሰጠ ነው፣ በሥጋዊ መገለጥ፣ እሱ በሰው ኃጢአት ደስ ስላለመሰኘቱ። ቅጣት ማለት ግለሰቡን ወደ እምነት መመለስ ነው። በዚህ ቁጥር ላይ ትይዩው የሚገልጸው ሥጋዊው ቅጣት የሚመለከቱትን እንደሚያስፈራ ነው፣ የቅርብ ወዳጆች እና ዘመዶች ቢሆኑ እንኳ።

ስለዚህ፣ ወደ ምርጫ ሲመጣ፣ በርካታ ዓይነቶች በነገሩ ላይ ይገኛሉ።

1. ምን ዓይነት አካላዊ መገለጫ?
2. መገለጫው ለምን?
3. ከሌሎች ቅርብ ከሆኑት ምላሹ ለምን?
4. እሱስ ዘይቤአዊ ነው ጥሬአዊ?

***መዝሙር ፡ 38፡13-22***

**13እኔ ግን እንደማይሰማ ደንቆሮ**
**አፉንም እንደማይከፍት ዲዳ ሆንሁ።**
**14እንደማይሰማ ሰው**
**በአፉም ተግሣጽ እንደሌለው ሰው ሆንሁ።**
**15አቤቱ፥ በአንተ ታምኛለሁና**
**አቤቱ አምላኬ፥ አንተ ትሰማኛለህ።**
**16ጠላቶቼ በእኔ ላይ ደስ እንዳይላቸው ብያለሁና፥**
**እግሮቼም ቢሰናከሉ ራሳቸውን በእኔ ላይ ከፍ ከፍ ያደርጋሉ።**
**17እኔስ ወደ ማንከስ ቀርቤአለሁና፥**
**ቍስሌም ሁልጊዜም በፊቴ ነውና።**
**18በደሌን እናገራለሁና፥**
**ስለ ኃጢአቴም እተክዛለሁ።**
**19ጠላቶቼ ሕያዋን ናቸው ይበረቱብኝማል፥**
**በጠማማነትም የሚጠሉኝ በዙ።**
**20ጽድቅን ስለ ተከተልሁ፥**
**በበጎ ፋንታ ከፉን የሚመልሱልኝ ይጠሉኛል።**
**21አቤቱ፥ አንተ አትጣለኝ**
**አምላኬ፥ ከኔ አትራቅ።**
**22አቤቱ መድኃኒቴ፥**
**እኔን ለመርዳት ፍጠን።**

**38፡13-22** ይህ አንጓ የወቅቱ ሁኔታ ድብልቅ አለው (ሕመም፣ ሥቃይ፣ ቁስለት) እና የወደፊቱ ተስፋ በያህዌ ምሕረት።

1. የወቅቱ የሥጋ ችግሮች
   ሀ. አይሰማም (ማለትም፣ የእነርሱን ስልቂያ እንደማይሰማ ይመስላል)፣ ቁ. 13፤ መዝ. 39፡2፡4
   ለ. አይናገርም (ማለትም፣ ለጠላቶቹ ምላሽ፣ ኢሳ. 53፡7)፣ ቁ. 13ለ
   ሐ. ለመሰናከል የቀረበ ነው፣ ቁ. 16ለ-17ሀ፤ ለችግር ዘይቤ፣ ዘዳ. 32፡35፤ የእግዚአብሔር መንገድ ቅን ነው፣ የተስተካከለ፣ ከማሰናከያ የጸዳ
   መ. በፊቱም ዘወትር በኀዘን ነው (ኃጢአቱ በእርሱ ላይ ከብዶበታል)፣ ቁ. 17ለ፤ መዝ. 51፡3
   ሠ. ጭንቀት ብቻ፣ ቁ. 18
2. ጠላቶቹ ያጠቃሉ፣ ቁ. 16፣ 19-20
   ሀ. እነርሱ እየበረቱና እየበዙ ነው፣ ቁ. 19ሀ
   ለ. ያላግባብ ይጠሉታል፣ ቁ. 19ለ
   ሐ. በመልካም ፈንታ ክፉ ይመልሱለታል፣ ቁ. 20፤ መዝ. 35:12፤ 109:5
   መ. እነርሱ ይቃወሙታል፣ መልካም በማድረጉ፣ ቁ. 20ለ
3. በያህዌ ፍቅር፣ ምሕረት፣ እና ይቅርታ መታመን
   ሀ. ተስፋ ("መጠበቅ፣" ቢዲቢ 403፣ ኬቢ 407፣ ሂፊልየተጠናቀቀ) በያህዌ፣ ቁ. 15ሀ፣ ኢዮብ 13:15፤ መዝ. 31:24፤ 33:22፤ 39:7፤ 42:5፡11፤ 43:5
   ለ. ያህዌ ጸሎቱን እንደሚመልስለት ያምናል፣ ቁ. 15ለ
   ሐ. ጠላቶቹ እንደማይሳካላቸውና በእርሱ መውደቅ እንደማይደሰቱ ያምናል ቁ. 16
   መ. ይጸልያል (ሁለት ተጽዕኖዎች፣ አንድ ተተኳሪ)

(1) አትተወኝ – ቢዲቢ 736፣ ኬቢ 806፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ *መዝ.* 9:11፤ 71:9፣18፤ 94:14፤ 119:8፤ ኢሳ. 49:14
(2) ከእኔ አትራቅ – ቢዲቢ 934፣ ኬቢ 1221፣ *ቃል* 1ያልተጠናቀቀ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ *መዝ.* 22:11፣19፤ 35:22፤ 71:12
(3) እኔን ለመርዳት ፍጠን – ቢዲቢ 301፣ ኬቢ 300፣ *ቃል* ተተኳሪ፣ *መዝ.* 22:19ለ፤ 40:13፤ 70:1፣5፤ 71:12፤ 141:1

**38፡18** ይህ *ሥነ-መለኮታዊ* ቁልፍ ነው፣ የዚህ *መዝሙር* (*መዝ.* 32፡5)። ንስሐ *ያመጣል*
1. ይቅርታን ከያህዌ (*መዝሙር* 51፤ 1 ዮሐንስ 1:9-2:1 ላይ ያለ ማስታወሻ)
2. ይቅርታ ለራስ
3. የኅብረት መመለስ ስሜት

ንስሐ እውቅና ይሰጣል
1. የሰው ኃጢአት የእግዚአብሔርን ሕግ መስበሩን
2. የያህዌ ባሕርይ ለይቅርታና ምሕረት

**38:19**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ጠማማነት"** |
| **አየተመት** | **"ያለ ምክንያት"** |
| **አእቅ** | **"ያላግባብ"** |
| **አኢመቅ፣ የተእመቅ** | **"ያለ ምክንያት"** |
| **አእት መጽሐፍ ቅዱስ** | **"ያለ አንዳች ምክንያት"** |

ኤምቲ "መኖር" የሚል አለው (□ייב ፣ ቢዲቢ 313)፣ *ነገር ግን* በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች *ሥሩን* ወደ □נב አሻሽለውታል፣ ቢዲቢ 336፣ *መዝ.* 35:19፤ 69:4። ይህም ከቀጣዩ ስንኝ ትይዩነት *ጋር* ይገጥማል፣ "በጠማማነት ጠሉኝ" (ቢዲቢ 1055)።

▣ **38፡20 "ጠላቶች"** ይህ የዕብራይስጥ *ሥር* ነው (ቢዲቢ 966) ከእርሱም "ሰይጣን" የሚለውን *ቃል ያገኘንበት*።

## ልዩ ርዕስ፡ ሰይጣን

በተለያዩ ምክንያቶች ይህ ርዕስ በጣም አስቸጋሪ ነው፡፡
1. ብሉይ ኪዳን ለደግነት ታላቅ ጠላት ብሎ አያስቀምጥም ነገር ግን የያህዊ አገልጋይና ለሰው ልጆች አማራጭ በመስጠት በፅድቅ ባለመሆኑ የሚከስ መሆኑን ነው፡፡
2. የክፋት ዋና ሃሳብ እየተስፋፋ የመጣው ኪዳን ባስነበረበት ዘመን ሥን ፅሁፍ ነበር፤ ይህም ሊስፋፋ የቻለው በፈሪሳዊያን ኃይማኖት (ዘራሽ ትራኒያንዝም) አማካኝነት ነበር፡፡ ይህም በተራው የረቢዎችን ኃይማኖት በከፍተኛ ሁኔታ ተፅዕኖ አሳድሮበታል፡፡
3. አዲስ ዲን የብሉይ ኪዳን ዋና ሐሳባችን የሚያስፋፋው በሙሉ በሙሉ ባይሆንም የተወሰኑትን መርጦ ነው፡፡

አንድ ሰው ከመፅሐፈ ቅዱስ አንፃር ክፋትን ለማጥናት ቢፈልግ፣ ስለክፋት የተለያዩ አመለካከቶኛ ወይም እሳቤዎተን ያገኛል፡፡

ይሁን እንጂ አንድ ሰው ከመፅሐፍ ቅዱስ ውጪ ወይም ተጨማሪ ከሚመለከቱት ከዓለም ወይም ከምስራቅ ኃይማኖቶች አንፃር ክፋትን የሚመረምር ከሆነ አብዛኛው የአዲስ ዲን ትምህርት በፋሪሳዊያን እና በግሪኩ ሮማን የመናፍስት አምልኮ ይሸፈናል ማለት ነው፡፡

አንድ ሰው በቅድሚያ ለመፅሐፍ ቅዱስ መለኮታዊ ስልጣን የሚገዛ ከሆነ የአዲስ ኪዳን መስፋፋት ሊታይ የሚገባው እንደ ቀጣይ መገለጥ ነው፡፡ ክርስትያኖች መፅሐፍ ቅዱሳዊውን ሐሳብ ለመለፅ ከአይሁድ ተረትና ምሳሌ መጠበቅ አለባቸው (ዳንቲ፣ ሚስተን)፡፡ በዚህ መረዳት ላይ ግራ መጋባትና ሚስጢራዊነት እንዳለ የማታመን ነው፡፡ እግዚአብሔር የመረጠው ሁሉንም የክፋት አቅጣጫዎች ለመግለጥ ብቻ አይደለም ነገር ግን የክፋትንም መሸነፍ ጥምር እንጂ፡-

በብሉይ ኪዳን አጠራር ሰይጣን ወይም ከሳሽ ከሶስት የተለያዩ ቡድኖች *ጋር* ይዛመዳል
1. የሰው ከሳሾች (1ሳሙ 29፡4፣ 2ሳሙ 19፡22፣ 1ነገ 11፡14-23-25፣ *መዝ* 109፡6)
2. የመላዕክት ከሳሾች (ዘሑል 22፡23፣ ዘካ 3፡1)
3. የክፊ መናፍስት ከሳሾች (ዜና 21፡1 22፡21 ዘካ 13፡2)

በዘፍ 3 ላይ የተጠቀሰው እባብ ሰይጣን መሆኑ የታወቀው በኃይለኛው የዝምታ ግዜ ነበር (የጥበብ መፅሐፍ 2፡23-24፣ 2ሔኖክ 31፡3) ከኋላም ቢሆን ይህ ሁኔታ በረቢዎች እንደአማራጭም አልታየም ነበር፡፡ የእግዚአብሔር ልጆች (ዘፍ 6) በሔኖክ 54፡6 ላይ መላህክት

ተብለው ተጠቅሰዋል፡፡ ይህን የምገልፅው *ሥን* መለኮታዊ ትክክለኛነቱን ለመንገር ሳይሆን ዕድገቱን ለማሳየት ነው፡፡

በአዲስ ኪዳን እነዚህ የብሉይ ኪዳን እንቅስቃሴዎች ስብዕና ካለው መልዕክት *ጋር* ይዛመዳል (ሰይጣን) ፡- 2ቆሮ 11፡3፣ ራዕይ 12፡9

ስብዕና ያለውን ክፋት በብሉይ ኪዳን ለመወሰን አስቸጋሪ ወይም የማይቻል ጉዳይ ነው (በአንተ እይታ በመመርኮዝ) ለዚህም አንድ ምክንያት የእስራኤል የአንድ አምላክ አምልኮ ነው፡፡ (1ነገ 22፡20-22፣ መክ 7፡14 ኢሳ 45፡7 አሞ 3፡6) ሁሉም መልካም ያልሆነ ነገር ከያህዊህ *ጋር* የተገናኘ ነበር፤ ልዩ እና ቀዳሚ መሆኑን ለማመልከት (ኡሳ 43፡11፣ 44፡6፣ 8፡24፣ 45፡56፣ 14፡18፣21፡22) የመረጃ ምንጬች እንደሚያመለክቱት (1) ኢዮብ 1-2 ሰይጣን ከእግዚአብሔር ልጆች አንዱ እንደሆነ (2) ኢሳ 24፣ ሕዝ 28 ትዕቢት የተሞሉትን የቅርብ ምስራቅ ነገስታት (ባቢሎን ጢሮስን) የሰይጣንን ትዕቢት ለማሳየት መጠቀሙ (1ጢሞ 3፡6)፡፡ ሕዝቅኤል የኤደን ገነትን የጢሮስን ንጉስ በሰይጣን ተምሳሌትነት ብቻ አልተጠቀመም (ሕዝ 28፡12-16) ነገር ግን የግብፅንም ንጉስ መልካሙንና ክፋውን እንደምታስታውቀው የእውቀት ዛፍ መስሏታል (ሕዝ 31) ይሁን እንጂ ኢሳ 14 በተለይም ቁ. 12-24 በትዕቢት ምክንያት የተነሳ የመላህክት አመፅን ለመግለፅ ይመስላል፡፡ እግዚአብሔር እያንዳንዱን የሳይጣን ባህሪ መግለፅ ቢፈልግ ኖሮ ይህ እንግዲህ በስራ ላይ ለማዋል በጣም ገዳዳ የሆነ አመለካከት ነው፡፡

አልፍሬድ ኢድርሻይም (The Life and Times of Jesus the Messiah፣ Vo. 2፤ ማውጫ 13 (ገፅ 748-763) እና ማውጫ 16 (ገፅ 770-776) እንደሚናገሩት የረቢዎች የአይሁድ ኃይማኖት በፋሪሳውያን የጣምራ ፍልስፍና እና ኢጋንታዊ ግምቶች በብዙ ተፅዕኖ

እንደደረሰበት ነው፡፡ ረቢዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ጥሩ የመረጃ ምንጮች ሊሆኑ አይችሉም፡፡ ኢየሱስ በምኩራብ ከሚሰጠው ትምህርት ለየት ይላል፡፡

ሁለቱ የኢራናዊያን አማልዕክት (ዱዋሊዝም) Aukiman እና Ormaza መልካም እና ክፉ በተጨማሪም የረቢዎች ሐሳብ ተደምሮ ያቅዊና ሰይጣን የሚሉትን አመጣ የክፋትን ዕድገት በሚመለከት በአዲስ ኪዳን ቀጣይነት ያለው መገለጥ አለ ነገር ግን ረቢዎች እንደሚያብራሩት አይደለም፡፡ ጥሩ ምሳሌ ሊሆን የሚችለው "በሰማያት ላይ ያለው ጦርነት" የሚለው ነው የሰይጣን ውድቀት አስፈላጊ ነው ነገር ግን ዝርዝሮች አልተሰጡም፡፡ የተጠቀሰው እንኳን በታዩ ራዕዮች ምክንያት የተሸፈነ ይመስላል፡፡ (ራዕ 12፡4፡7፣ 12-13) ምነም እንኳን ሰይጣን የተሸነፈና የተጣለ ቢሆንም አሁንም የእግዚአብሔር ባሪያ ሆኖ ይሰራል (ማቴ 4፡1፣ ሉቃ 22፡31-32፣ 1ቆሮ 5፡5 1ጢሞ 1፡20)፡፡

በዚህ አቅጣጫ ላይ ያለንን መደነቅ ልንገታው ይገባል፡፡ በግላችን የሚገጥመን ክፋትና ፈተና አለ ነገር ግን ያለን አንድ አምላክ በቻ ስለሆነ የሰው ልጅ ለሚወስደው ማናቸውም ምርጫ ኃላፊነት አለበት፡፡ ከደህንነት በፊትም ሆነ በኋላ መንፈሳዊ ውግያ አለ፡፡ ድል ሊመጣና ሊጠበቅ የሚችለው በእግዚአብሔር ብቻ ነው፡፡ ክፋት ተሸንፏል ደግሞም ወደፊትም ይወገዳሉ፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ያህዌ ኃጢአተኛ ተከታዮቹን ይቀጣልን፣ በዚህ ሕይወት?
2. ቁጥር 4 የብዙ ኃጢአት ኑዛዜ ነውን ወይስ የሰዎች ሁሉ ኃጢአተኝነት ማስረገጫ መንገድ፣ በጥሬው?
3. ሥጋዊ ችግሮችን ዘርዝር፣ ንስሐ ካልገቡት ኃጢአት ጋር የሚያያዘውን።
4. "ቁስል" የሚለውን ቃል ቁጥር 11 ላይ ግለጽ። ያንተ ገለጻ ሌሎች በእርሱ ላይ ያላቸውን አቋም ያብራራልን?
5. የ"እግር መንሸራተት" የሚለው ምናብ ከኃጢአት ሕይወት ጋር እንዴት ይዛመዳል?
6. ቁጥር 18 እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?

# መዝሙር 39
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የሕይወት ከንቱነት<br>ኤምቲ መግቢያ "ለመዘምራን አለቃ፣ ለኤዶታም" የዳዊት መዝሙር | ጸሎት ለጥበብና ለይቅርታ | ጸሎት በሕመም ጊዜ ለፈውስ (ሰቆቃ) | የመከረኛ ኑዛዜ | የሰው ልጆች ከንቱነት በእግዚአብሔር ፊት |
| 39:1-6 | 39:1-3 | 39:1-6 | 39:1-4 | 39:1-2 |
| | | | | 39:3-4 |
| | 39:4-6 | | | |
| | | | 39:5-6 | 39:5-6 |
| 39:7-11 | 39:7-11 | | | |
| | | 39:7-10 | 39:7-11 | 39:7-9 |
| | | | | 39:10-11 |
| | | 39:11 | | |
| 39:12-13 | 39:12-13 | 39:12-13 | 39:12-13 | 39:12-13 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. በመጀመሪያ ይህ መዝሙር ያደነጋግራል። እሱ የሚጀምረው በተሸፈነ የአጻጻፍ ብልሃት ነው፣ ባመዣኙ እንደ መለኮታዊ ምሥጢር፣ እሱም በውጭ ያሉት ሊካፈሉት/ሊረዱት የማይቻል (ግን አሁንም ኃጢአተኛ የሆኑ) ታማኝ ከያህዌ ጋር ከሚራመድ በቀር፣ ቁ. 8።

ለ. መለኮታዊው ምሥጢር እና የሰው ጥያቄ የሰው ሕይወት ቋሚ አለመሆን ነው። የሰው ልጅ እጅግ ደካማ፣ ተሰባሪ፣ ጊዜያዊ፣ አላዋቂ፣ እና ዘወትርም እርሱ/እርሷ አስተሳሰባቸውን በተሳሳተ ነገሮች ላይ የሚያተኩሩ ነው (ዝከ. ቁ. 6፣ 11)።

ሐ. ይህ መዝሙር በብዙ መንገዶች መክብብን ያስታውሰኛል (የሕይወትን ከንቱነት፣ አምላክ ከሌለበት)። መዝሙረኛው የራሱን ባሕርይ ይገልጻል፣ በአስገራሚ መንገዶች።
1. እንደ ባዕድ፣ ቁ 12
2. እንደ መጻተኛ፣ ቁ. 12

መ. ቁጥር 13 ለእኔ አሁንም ምሥጢራዊ ነው። የውድቀታችን ሁኔታ አስፈሪው እውነት የሚሆነው
1. በእግዚአብሔር ተማርከናል
2. ቅድስናው ያስፈራናል፣ ወደ ኋላ ያስፈገፍገናል፣ ሁሉም በአንድ ጊዜ!
   ርግጠኛ የሆነ የአእምሮ ግጭት አለ፣ በሰዎች ሁኔታ ተለዋዋጭነት እና በአምላካችን ዘላለማዊነት መካከል፣ እሱም ለኅብረት የፈጠረን። ደስተኛ መሆን አንችልም፣ እሱን ሳናውቅና ሳናፈቅር። እኛ ግን ተሰባሪና ጊዜያዊ ነን። እሱ ፍጹምና ዘላለማዊ ነው።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

***መዝሙር ፤ 39፥1-6***

***ለመዘምራን አለቃ፥ ለኤዶታም የዳዊት መዝሙር።***
***1 በአንደበቴ እንዳልስት***
***መንገዴን እጠብቃለሁ***
***ኃጢአተኛ በፊቴ በተቃወመኝ ጊዜ***
***በአፌ ላይ ጠባቂ አኖራለሁ አልሁ።***
***2 ከዝምታ የተነሣ እንደ ዲዳ ሆንሁ፥***
***ለበጎ እንኳ ዝም አልሁ፥***
***ቍስሌም ታደሰብኝ።***
***3 ልቤም በውስጤ ሞቀብኝ***
***ከማሰቤም የተነሣ እሳት ነደደ፥***
***በአንደበቴም ተናገርሁ።***
***4 አቤቱ፥ ፍጻሜዬን አስታውቀኝ፥***
***የዘመኔ ቍጥሮች ምን ያህል እንደ ሆኑ፥***
***እኔ ምን ያህል ወደ ኋላ እንደምቀር አውቅ ዘንድ።***
***5 እነሆ፥ ዘመኖቼን አስረጀሃቸው***
***አካሌም በፊትህ እንደ ኢምንት ነው።***
***ሕያው የሆነ ሰው ሁሉ በእውነት ከንቱ ብቻ ነው። ሴላህ***
***6 በከንቱ ይታወካል እንጂ***
***በእውነት ሰው እንደ ጣላ ይመላለሳል***
***ያከማቻል የሚሰበስብለትንም አያውቅም።***

**39፥1-6** ኀጢአተኞች ለዛሬ ብቻ ይኖራሉ፣ ለራሳቸው፣ ታማኝ ተከታይ ግን ለያህዌ እንደሚኖርና እንደሚናገር ያውቃል። ሆኖም፣ ያለ መንፈስ ርዳታ (ዮሐንስ 6፡44፣65) ኃጢአተኞች ሊደርሱበት አይችሉም

1. የገዛ ራሳቸውን መንፈሳዊና ሥጋዊ ሁኔታ
2. የእግዚአብሔርን እውነት

እነርሱ የተሳሳቱ ጥያቄዎችን ይጠይቃሉ፣ እናም በተሳሳቱ ነገሮች ላይ ያተኩራሉ።

**39፥1 "እጠብቃለሁ"** ግሡን ተገንዘቡ (ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ *ቃል ተጓዳኝ*) መደገሙን። መዝሙረኛው አስተሳሰቡን መናገር አይኖርበትም፣ ስለ ሕይወትና ስለ እግዚአብሔር፣ በማያምኑ ጽኑአን ፊት (ማለትም፣ ማቴ. 7፡6)። ይህ አንጓ የጽሑፍ ማጣራት የተደረገበት ሊሆን አይችልም፣ እንደ ቅዱስ ቃሉ በተቃርኖ ለሌሎች ስለ መመስከር። ነገር ግን እሱ እውነት ነው፣ አንዳንድ ጉዳዮች፣ አንዳንድ ዶክትሪኖች በቅድሚያ ከንግግራችን ላይ፣ ሊወገዱ ይገባል፣ በማያምኑ ፊት፣ ሊኖር ከሚችለው አለመረዳት ወይም ውዥንብር የተነሣ። መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርዕዮተ-ዓለም ይጠይቃል

1. መንፈስ (ዮሐንስ 6፡44፣65)
2. የሚቀበል ልብ (ማቴዎስ 13)
3. መገለጥ፣ ሊረዱት በሚችሉት መልኩ
4. ጊዜ/ጥረት

የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 374) ዝምታውን የሚተረጉመው መዝሙረኛው ስለ ሕይወቱ ማማረር አለመፈለጉን ነው፣ በክፉዎች ፊት።

◘ **"በአንደበቴ እንዳልስት"** ኃጢአት እዚህ መረዳት የሚገባው በዐውደ-ጽሑፉ ነው፣ እውነትን እንደመናገር ነው፣ ኃጢአተኞች ሊቀበሉት እንደማይችሉት (ማቴ. 7፡6)።

**39፥2-3** ባጠቃላይ መዝሙረኛው ራሱ በእነዚህ ጉዳዮች ላይ ለማሰብ አይሞክርም። ነገር ግን መገለጥ ወደ እግዚአብሔር እንዲናገር ምክንያት ይሆነዋል፣ ጥያቄውንና ማሰቡን፣ ስለ ሰው ሕይወት አጭርነትና ተለዋጭነት።

**39፥2 "ለበጎ እንኳ ዝም አልኩ"** በኤምቲ ይህ ሐረግ "ለሚጠቅም እንኳ ዝም አልኩ" ይላል (ማለትም፣ ያለ ስኬት፤ "ያለ መልካም፣" ቢዲቢ 373)። ይህ አሻሚ ነው፣ እናም የተለያዩ ትርጉሞች በተለያየ መንገድ ይገልጹታል። ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ እሱ የሚያመለክተው የመዝሙረኛውን ለመናገር መሻት ሲሆን፣ ነገር ግን ማድረግ እንደሌለበት ይሰማዋል። የእሱ ለመናገር እምቢ ማለት ሁኔታውን አያግዝም።

ሕይወት እጅግ አጭር ከሆነ፣ የወደቁ ሰዎች በምን ላይ ማተኮር ይኖርባቸዋል? የጻድቅና ጻድቅ ያልሆነው ዕጣ ፈንታ አንድ ይመስላል (መክ. 2፡14-16፣19፣26፤ 9፡2-3)።

**39፥3 "እሳት ነደደ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 128፣ ኬቢ 145፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) ተመሳሳይ ነው፣ ኤርምያስ የእግዚአብሔርን ቃል ለመናገር የደረገውን ጉትጎታ ከሚገልጸው ጋር (ኤር. 20፡9)።

**39፥4-6** እነዚህ መዝሙረኛው "በጥልቀት ያሰበባቸው" ጉዳዮች ናቸው (ቢዲቢ 211፣ መዝ. 5፡1) ስለ

1. ሕይወት ርግጠኛ አለመሆን
2. ሕይወት አጭር መሆን

3. የተሳሳተ አትኩሮት (ማለትም፣ ዝና፣ ብልጥግና) የሕይወት
4. ሕይወት አድሏዊነት

**39፡5 "አካሌም"** ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 381) ከበርካታ የዕብራውያን መለኪያዎች አንዱ ነው፣ ከሰው አካል።
1. የተዘረጋ ክንድ
2. ከጣት ጫፍ እስከ ክርን
3. የተዘረጉ ጫፎች
4. አራቱም ጣቶች አንድ ላይ (ጥርኝ)
5. አንዲት ነጠላ ጣት

## ልዩ ርዕስ፡ ክንድ

ሁለት ዓይነት ክንዶች (መለኪያዎች) አሉ (ቢ.ዲ.ቢ. 52፣ ኬ.ቢ. 61) በመጽሐፍ ቅዱስ። መደበኛው ክንድ የመካከለኛ ሰው ረጅሙ ጣት እስከ ክንዱ ድረስ ያለው ርቀት ሲሆን፣ እሱም ዘወትር 18 ኢንች ያህል ነው (ዘፍ. 6፡15፤ ዘጸ. 25፡10፣17፣23፤ 26፡2፣8፣13፣16፤ 27፡1፣9፣12፣13፣14፣16፣18፤ ዘኍ. 35፡4፣5፤ ዘዳ. 3፡11)። ደግሞም ረጅም ክንድ አለ (ንጉሣዊ ክንድ) ለግንባታ ሥራ የሚውል (ማለትም፣ የሰሎሞን መቅደስ)፣ እሱም በግብፅ የተለመደ (ማለትም፣ 21 ጣቶች)፣ ፍልስጥኤም (ማለትም፣ 24 ጣቶች)፣ እናም አንዳንዴ ባቢሎን (ማለትም፣ 30 ጣቶች)። እሱም 21 ኢንች ርዝማኔ ነበረው (ሕዝ. 40፡5፤ 43፡13)።

የጥንቶቹ የሰውን አካል ክፍሎች ለመለኪያነት ይጠቀሙ ነበር። የጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ሕዝቦች ይጠቀሙ የነበረው፡
1. ከክርን እስከ መካከለኛው ጣት ጫፍ (ክንድ)
2. ከተዘረጋው አውራ-ጣት እስከ ትንሿ ጣት (ርቀት፣ ዘዳ. 28፡16፤ 39፡9፤ 1 ሳሙ.17፡4)
3. አራቱ ጣቶች ተገጣጥመው ያለው ርዝመት፣ የተገጠሙ ጣቶች (ቡጢ፣ ዘጸ. 25፡25፤ 37፡12፤ 1 ነገ. 7፡26፤ 2 ዜና. 4፡5)
4. የጣት መካከለኛው መጋጠሚያ ርዝመት፣ (ጥርኝ፣ ኤር. 52፡21)

ክንድ (ቢ.ዲ.ቢ. 52፣ ኬ.ቢ. 61) ፍጹም መለኪያ አልነበረም፣ ነገር ግን ሁለት መሠረታዊ ርዝመቶች ነበሩት።
1. የሙሉ ሰው ክርን እስከ መካከለኛው ጣት ድረስ (18 ኢንች ያህል፣ ዘዳ. 3፡11)
2. ንጉሣዊ ክንድ ትንሽ ከፍ ይላል (20 ኢንች ያህል፣ 2 ዜና. 3፡3፤ ሕዝ. 40፡5፤ 43፡13)

◘ ***"የሕይወት ዘመኔም በፊትህ እንደ ኢምንት ነው"*** ይህ ማለት ያህዌ ክብካቤ እንደማያደርግ የሚያስረግጥ አይደለም ነገር ግን የሰው ሕይወት አጭር እና ትርጉም-አልባ መሆኑን ነው፣ ከያህዌ ጋር ሲነጻጸር (ኢሳ. 40፡15)።

◘ **"ከንቱ እስትንፋስ"** ይህ ሐረግ (ቢ.ዲ.ቢ. 481 አወቃቀር ቢ.ዲ.ቢ. 210 I) ሌለኛው ፍች ነው ለመክብብ (መክ. 1፡2፤ 12፡8፤ "እንፋሎት፣" "ትንፋሽ፣" "ከንቱነት")። ይህ ቃል ሠላሳ ጊዜ መክብብ ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እናም ዘጠኝ ጊዜ ብቻ መዝሙር ላይ (መዝ. 39፡5፣6፣11፤ 144፡4) እና ሦስት ጊዜ ምሳሌ ላይ።

◘ **"ሴላህ"** *መዝ.* 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻና መግቢያ ለመዝሙር VII ተመልከት።

**39፡6 "ውልብታ"** ይህ በጥሬው "ጥላ" ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 853)። እሱም ደመናትን ሊጠቅስ ይችላል፣ ነገር ግን በመደበኝነት በዘይቤአዊ መልኩ ጥቅም ላይ የሚውለው ለሕይወት ጊዜያዊነት ነው (ኢዮብ 8፡9፤ 14፡2፤ መዝ. 102፡11፤ 109፡23፤ 144፡4)። ይህም የዚህ መዝሙር ርዕሰ-ጉዳይ ነው! መዝሙር 8 መልካም ሥነ-መለኮታዊ ትይዩ መሆን ይችላል።

◘ ***"ሀብትን ያከማቻል የሚሰበስብለትንም አያውቅም"*** ይህ እጅግ ተመሳሳይ ነው፣ ለቆሄለች *(Qohelech)* አስተሳሰብ፣ መክ. 2፡18-23።
አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 778) የተሻለ አስተያየት አለው፣ በዚህ ቁጥር ላይ።
"ደግሞም ለመክብብ እንደማጠቃለያነት ሊያገለግል የሚችል።"

### መዝሙር ፡ 39፡7-11

**[7]አሁንስ ተስፋዬ ማን ነው? እግዚአብሔር አይደለምን?**
**ትዕግሥቴም ከአንተ ዘንድ ነው።**
**[8]ከኃጢአቴ ሁሉ አድነኝ፥**
**ለሰነፎችም ስድብ አታድርገኝ።**
**[9]አንተ ሠርተኸኛልና**
**ዝም አልሁ አፌንም አልከፈትሁም።**
**[10]መቅሠፍትህን ከእኔ አርቅ፥**
**ከእጅህ ብርታት የተነሣ አልቆአለሁና።**
**[11]በተግሣጽህ ስለ ኃጢአቱ ሰውን ዘለፍኸው፥**
**ነፍሱም እንደ ሸረሪት ድር ታልቃለች**
**በእውነት ሰው ሁሉ ከንቱ ነው። ሴላህ።**

**39፡7-11** ይህ አንጓ ሁለንተናዊ ማጠቃለያ ነው፣ ያህዌ እንዴት አድርጎ ታማኝ ተከታዮቹን እንደሚይዝ፣ በዚህ በወደቀ ዓለም በጥያቄዎችና በውዥንብር ሕይወት መካከል።

1. ያህዌን ይጠብቃሉ
2. ያህዌን ተስፋ ያደርጋሉ (ቁ. 1፣2 ሥነ-መለኮታዊ ቁልፍ ነው፣ በእኛ ምሥጢራዊና የአጭር ጊዜ ሕይወት)
3. እንዲታደጋቸው ወደ ያህዌ ይጸልያሉ – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ ሂፊል ተተኳሪ (መዝ. 38፡10)
4. ሰነፍ እንዳይሆኑ ይጸልያሉ – ቢዲቢ 962፣ ኬቢ 1321፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
5. ያህዌ ቃላችንንና ሕይወታችንን ይመራል (መዝሙር 139)
6. የያህዌ ፍርድ እንዲነሣ ይሻሉ — ቢዲቢ 693፣ ኬቢ 747፣ ሂፊል ተተኳሪ

ቁጥር 10-11 የያህዌ ድርጊቶች ምክንያት ተመልክቷል።

1. ያህዌ በሕይወታቸው ንቁ ነው
2. የያህዌ ፍርዶች ተግሣጻዊ ናቸው፣ የሚያሳዝኑ ሳይሆኑ
3. ያህዌ አንዳንድ ነገሮችን ይወስዳል፣ ከእርሱ ይልቅ የምንታመንባቸውንና የምንያዝባቸውን! ሁሉም ነገር ከያህዌ በቀር የአጭር ጊዜ ነው! አገኛችሁት?!

**39፡10**
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**
**ጀፒኤስኦኤ** **"መቅሠፍት"**
**አየተመት** **"ነውጥ"**
**አእቅ፣ የተእመቅ** **"ምት"**
**አኢመቅ፣ LXX** **"ግርፊያ"**

የዕብራይስጡ ስም (ቢዲቢ 619፣ መዝ. 38፡11 ላይ ማስታወሻ ተመልከት) ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ከያህዌ ለተላከ ሕመም ነው።

1. መቅሠፍት – ዘፍ. 12፡17፤ ዘጸ. 11፡1፤ 1 ነገ. 8፡37፤ መዝ. 38፡11፤ 39፡10
2. ምት/ነውጥ – መዝ. 89፡23፤ ኢሳ. 53፡8
3. ግርፊያ – መዝ. 89፡23

ያህዌ ሊያስወግደው ይችላል፣ ስለ ላከው! እሱም ዘወትር አዳጋች ነው፣ የማይቻል ባይሆን እንኳ፣ የሕመምን፣ ሁነትን፣ ቀውስን፣ ወዘተ ምንጭ ለማወቅ፣ በዚህ ሕይወት። የብኪ ሥነ-መለኮት ሁሉንም ምክንያቶች ለያህዌ ይሰጣል፣ እንደ ሥነ-መለኮታዊ መንገድ አሀዳዊነትን ለማስረገጥ። ነገር ግን ቀጣይነት ካለው ከአኪ መገለጥ አኳያ በርካታ አማራጮች ይነሣሉ።

1. እግዚአብሔር ነገሮችን ይልካል
   ሀ. ለቅጣት
   ለ. ለመንፈሳዊ እድገት (ዕብ. 5፡8)
2. እግዚአብሔር ይፈቅዳል (ባይልክም) ነገሮች እንዲከሰቱ
3. የምንኖረው በወደቀው ዓለም ነው፣ መጥፎ ነገሮች በሚሆኑበት (ስታስቲካዊ ክፉ)

በእምነት መርጫለሁ፣ (መዝሙረኛው እንዳደረገው)፣ እግዚአብሔርን ለማመን፣ ተስፋ ለማድረግ፣ እና ለመጠበቅ (መዝ. 38፡15፤ 39፡7)፣ በምሥጢራዊው፣ ፍትሐዊ ባልሆነው፣ ዘወትርም የሕይወት ክፉ ሁነቶች በሚከሰቱበት መካከል። እኔን አይገባኝም "ለምን" ወይም "ለምን አሁን" ወይም "ለምን ይሀ" ወይም "ለምን ያህል፣" እንደሆነ፣ ነገር ግን በእምነት አደርጋለሁ፣ እግዚአብሔርን በማመን፣ ከእኔ ጋር እንደሆነ፣ ለእኔ እንደሆነ፣ እናም ለሁሉም ነገሮች ዓላማና ውጤታማነት ሊኖር እንደሚችል (ሮሜ. 8፡28-30፣31-39)! እሱም ርዕዮተ-ዓለም፣ የእምነት አቋም፣ ሥነ-መለኮታዊ መግለጫ ነው!

▣ **"የእጅህ ብርታት"** እጅ የድርጊት ኃይል ፈሊጥ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 7፡3-4 ላይ)። ስለ ሥነ-መለኮታዊ ጉዳይ መዝ. 32፡4 እና 38፡ 2 ተመልከት። እግዚአብሔር እንደሚገሥጽ፣ እንደሚወድ ወላጅ አስደናቂ ዘይቤ ነው (ምሳ. 3፡11-12)። እሱ በሕይወታችን ላይ ንቁ ነው፣ ምክንያቱም እሱ ራሳችንንም ሆነ ሌሎችን እንድናጠፋ ስለማይፈልግ። የ"እጅ" ተግሣጽ አዎንታዊ ዓላማ አለው (ዕብ. 12፡5-13)።

**መዝሙር ፡ 39፡12-13**

**12አቤቱ፥ ጸሎቴን ስማ፥ ጩኸቴንም አድምጥ፥**
**ልቅሶዬንም ቸል አትበለኝ**
**እኔ በምድር ላይ መጻተኛ ነኝና፥**
**እንደ አባቶችም እንግዳ ነኝና።**
**13ወደማልመለስበት ሳልሄድ**
**ዐርፍ ዘንድ ተወኝ።**

**39፡12-13** በመዝሙራት እንደተለመደው ሁሉ፣ የሚዘጋው በጸሎት ጥያቄ ነው።

1. አድምጥ – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ ቃል ተተኳሪ
2. ስማ – ቢዲቢ 24፣ ኬቢ 27፣ ሂፊልተተኳሪ
3. ዝም አትበል – ቢዲቢ 361፣ ኬቢ 357፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 28፡1፤ 35፡22፤ 83፡1፤ 109፡1
4. አታተኩርብኝ – ቢዲቢ 1043፣ ኬቢ 1609፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ ኢዮብ 7፡17-19፤ 10፡20-21፤ 14፡6 ተመልከት
5. ጥቂት ዐርፍ ዘንድ – ቢዲቢ 114፣ ኬቢ 132፣ ሂፊል ተጓዳኝ፣ ኢዮብ 9፡27፤ 10፡20 ተመልከት

**39፡12** የዚህ ቁጥር የመጨረሻዎቹ ሁለቱ ስንኞች በመካከል ያሉትን ተቃርኖች ይመለከታሉ

1. የተለዩ የኪዳን ሕዝቦች

2. የኃጢአተኞች ቀጣይነት ያለው አጭር ሕይወት (1 ዜና. 29:15፤ መዝ. 119:19፣54፤ ዕብ. 11:13፤ 1 ጴጥ. 2:11)።
ይህ የብኪ ጭጋግ (ያልጠራ ነገር) እንደሆነ አስታውስ። የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል እነዚህን አብዛኞቹን ጉዳዮችና ጥያቄዎች ይመለከታቸዋል፣ ስለ ሕይወት፣ ስለ ዓላማ፣ እና ዘላለማዊነት!

▣ **"እንግዳ ነኝና"** ይህ ቃል/ጽንሰ-ሐሳብ እኔን ያሳስበኛል። እሱም አንዱ እግዚአብሔርን የማያውቀውን የሚጠቅስ ይመስላል ወይም በእግዚአብሔር ያልታወቀውን። ነገር ግን ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ እሱ የሚያመለክተው በድንኳን ያለ እንግዳ ነው፣ አንድ ወይም ሁለት ሌሊቶችን አሳልፎ የሚጓዝ። እሱም ለዘይቤአዊ ቋንቋ ሌለኛው ምሳሌ ነው፣ የሰው ሕይወት ጊዜያዊ መሆኑን የሚገልጽና ጸጸቱን።

**39፡13** ከያህዌ ቅድስና አኳያ፣ ይህ ሕይወት ችግር ያለበት ሆኗል (ኢዮብ 14፡6)። ያህዌን ለመምሰል ያለው ስበት (ማቴ. 5፡48፤ ሌዋ. 19፡2) እጅግ ጽኑ ሆኗል። በኢየሱስ ብቻ ነው ለእኛ ሰላም ሊመጣልን የሚችለው፣ በመገኘቱ እንድንሆን (ማለትም፣ መተው፣ ማለትም ከያህዌ ፍርድ ጋር በተያያዘ፣ ኢዮብ 7:19፤ 14:6፤ ኢሳ. 22:4) ከቅዱሱ እግዚአብሔር ጋር!

ከዚህ ቁጥር የተነሣ፣ የጴጥሮስ ጥያቄ፣ ሉቃስ 5፡8 ላይ ያለው ስሜት የሚሰጥ ይመስላል!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙረኛው በኃጢአተኞች ፊት ለምን ዝም ማለት ፈለገ (ቁ. 1)?
2. የቁጥር 4ን አንድምታ በገዛ ራስህ ቋንቋ አብራራ።
3. "ክንድ (የሰው አካል መስፈሪያ)" ምንድነው?
4. ቁጥር 11ለን አብራራ። ያህዌ ከተከተታዮቹ መካከል የአንዱን የከበረ ነገር ሁሉ ለምን ይወስዳል?
5. ቁጥር 11ሐ ያህዌ ለግለሰብ ሰዎች እንደማይጠነቀቅ የሚያመላክት ነውን?
6. ቁጥር 12፣ ሐ እና መ ምን ማለት ነው? ለያህዌ እንግዶች ነንን?
7. የቁጥር 13ን አንድምታ ፍች በገዛ ራስህ ቋንቋ አብራራ።

## መዝሙር 40
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር አገልጋዩን ይደግፋል<br><br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>"ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር" | እምነት በፈተና ላይ ያጸናል | ከችግር ለመዳን ምስጋና፣ ከዕርዳታ ጸሎት ጋር | የምስጋና መዝሙር | የምስጋና መዝሙርና የዕርዳታ ጸሎት |
| 40:1-3 | 40:1-3 | 40:1-3 | 40:1-3 | 40:1 |
| | | | | 40:2 |
| | | | | 40:3 |
| 40:4-5 | 40:4-5 | 40:4-5 | 40:4-5 | 40:4 |
| | | | | 40:5 |
| 40:6-8 | 40:6-8 | 40:6-8 | 40:6-8 | 40:6-7ሀ |
| | | | | 40:7ለ-8 |
| 40:9-10 | 40:9-10 | 40:9-10 | 40:9-10 | 40:9-10 |
| 40:11-12 | 40:11-12 | 40:11-12 | 40:11 | 40:11 |
| | | | የዕርዳታ ጸሎት | |
| | | | 40:12-15 | 40:12 |
| 40:13-17 | 40:13-15 | 40:13-15 | | 40:13-14ሀ |
| | | | | 40:14b-15 |
| | 40:16-17 | 40:16-17 | 40:16-17 | 40:16 |
| | | | | 40:17 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 40፡1-3**

**1ቆይቼ እግዚአብሔር ደጅ ጠናሁት፥**
**እርሱም ዘንበል አለልኝ ጩኸቴንም ሰማኝ።**
**2ከጥፋት ጕድጓድ ከረግረግም ጭቃ አወጣኝ፥**
**እግሮቼንም በድንጋይ ላይ አቆማቸው፥ አረማመዴንም አጸና።**
**3አዲስ ዝማሬን ለአምላካችን ምስጋና በአፌ ጨመረ**
**ብዙዎች ያያሉ ይፈሩማል፥**
**በእግዚአብሔርም ይታመናሉ።**

**40፡1-3** መዝሙረኛው ያህዌን ያመሰግናል ስላለፈው የማዳን ሥራው። ያህዌ ለጸሎቱ ምላሽ ሰጥቶታል (ማለትም፣ "አዘንብሏል" ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ ቃል ያልተጠናቀቀ እና "ሰምቶታል፣" ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ ቃል ያልተጠናቀቀ)።

ያህዌ አድርጓል
1. ከጥፋት አዘቅት ውስጥ አውጥቶታል ("የሁከት/የጫጫታ አዘቅት፣" ቢዲቢ 92 አወቃቀር ቢዲቢ 981፣ መዝ. 69:2፤ ይህም የውኃ ምናባዊ ሞት ሊሆን ይችላል (መዝ. 18:4) ወይም ጎርፍ (መዝ. 18:16)
2. ከዳጥ ጭቃ ውስጥ አውጥቶታል
   ሀ. በመንገድ ላይ ላለ ጭቃ ጥቅም ላይ የዋለ – 2 ሳሙ. 22:43፤ ሚኪያስ 7:10፤ ዘካ. 9:3፤ 10:5
   ለ. በመያዣ ውስጥ ላለ ጭቃ ጥቅም ላይ የዋለ – ኤር. 38:6
   ሐ. ለጭንቀት ዘይቤ ጥቅም ላይ የዋለ – መዝ. 40:2፤ 69:14 ("ጉድጓድ" ደግሞም 69:15 ላይ ተጠቅሷል)
   መ. ሲኦልን ሊጠቅስ ይችላል (ማለትም፣ ሞት፣ የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ. 381)
3. እግሮቹን በዐለት ላይ አደረገ አረማመዱን ለማጽናት – መልካም፣ ታማኝ የኪዳን ተከታዮች የሚባሉት በቀና፣ በተስተካከለ፣ ግልጽ በሆነ መንገድ የሚራመዱት ናቸው (መዝ. 17:5፤ 18:36፤ 37:31፤ 44:18፤ 69:9፤ 73:2፤ 94:18፤ Job 23:11፤ 31:7)
4. በአፌም አዲስ ዝማሬን አኖረ፣ የምስጋና ዝማሬ – አዲስ ዝማሬዎች ባህላዊ መንገዶች ናቸው፣ ለያህዌ የማዳን ድርጊቶች እውቅና የመስጠትና የማመስገን (ዘጸአት 15፤ መሳፍንት 5፤ ዘዳግም 32)፤ መዝ. 33:5 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፤ ደግሞም መዝ. 96:1፤ 98:1፤ 144:9፤ 149:1፤ ኢሳ. 42:10፤ ራዕ. 5:9፤ 14:3 ላይ ያለውን ማስታወሻ

ያህዌ መዝሙረኛውን ያዳነበት ዓላማ፣ ለአንድ ሰው የሆነ የተለየ አያያዝ አይደለም፣ ነገር ግን የእርሱን የኪዳን ተከታዮች ለመባረክና ለመጠበቅ እንጂ፣ ስለሆነም ሌሎች (ማለትም፣ "ብዙዎች፣" ቢዲቢ 912 I) የኪዳኑ ተከታዮች እንዲሆኑ እንጂ።
1. ተመልከት – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
2. ፍራ – ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
3. ታመን – ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*

**40፡1 "በትዕግሥት ይጠብቃሉ"** ይህ ያልተወሰነ ፍጹም ነው እና የተጠናቀቀ ግሥ፣ ከተመሳሳይ ሥር (ቢዲቢ 875፣ ኬቢ 1082) እምቅነትን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ።

▣ **"አዘንበል"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ cf. መዝ. 17:6፤ 88:2) ፍችው "ማዘንበል" ነው። ምናባዊ ምስያው አንድም ያህዌ ጆሮውን ማዘንበሉ፣ አጥርቶ ለማድመጥ፣ ወይም ያህዌ ለማድመጥ ማዘንበሉ ነው (ኢዮብ 15፡29)።

**40፡2 "ዓለት"** መዝ. 18፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

## መዝሙር ፡ 40፡4-5

**[4]እግዚአብሔርን የታመነ**
**ወደ ትዕቢተኛና ወደ ሐሰተኛ ያልተመለከተ ሰው ምስጉን ነው።**
**[5]አቤቱ አምላኬ፥ ያደረግኸው ተአምራት ብዙ ነው፥**
**አሳብህንም**
**ምንም የሚመስለው የለም**
**ባወራም ብናገርም**
**ከቍጥር ሁሉ በዛ።**

**40፡4-5 "እንዴት ምስጉን ነው"** ይህ የዚህ አንጓ ዋነኛ ሐሳብ ነው። ይህ ቃል (ቢዲቢ 80) 26 ጊዜ በመዝሙራት ጥቅም ላይ ውሏል። ሙሉ ማስታወሻውን መዝ. 1፡1 ላይ ተመልከት። መዝሙር 41 በዚህ ሐረግ ነው የሚጀምረው። እሱም ባብዛኛው መዝሙር እና ምሳሌ ላይ ነው ጥቅም ላይ የሚውለው (ማለትም፣ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ)፣ እሱም በስኬታማና በብልጽግና ሕይወት ላይ የሚያተኩር።

ለተባረከ አቋም የተሰጡት ምክንያቶች
1. *መታመኛውን ያህዌ ላይ ያደረገ*
2. *ወደ ትዕቢተኛ ያልተመለከተ* (ቢዲቢ 815፣ ኬቢ 937፣ *ቃል የተጠናቀቀ*) (LXX፣ አየተመት፣ አእቅ ቁ. 2፣3 ተመልከት፣ ጣዖታትን የሚጠቅሱ ናቸው)
3. *ያልተመለከተ* (ቢዲቢ 962፣ ኬቢ 1312፣ *ቃል አንቀጽ፣ ቃሉ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ*)

ቁጥር 5 ላይ የያህዌ አስተዋጽዖ ተዘርዝሯል።
1. *ተአምራቶችህ ብዙ ናቸው* (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9፡1 ላይ እና መዝ. 40፡5 ላይ ያለውን ማስታወሻ)
2. *ሐሳቡ ብዙ ነው፣ ለኪዳኑ ሕዝብ*
3. *ማንም የሚመስለው የለም* (መዝ. 16:2፤ ኢሳ. 6:8-10፤ ማለትም፣ አሀዳዊነት፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 2:7 ላይ)
4. *ተአምራቱም ሐሳቡም ከቁጥር ሁሉ በዛ*
   ሀ. ቢነገርም – ቢዲቢ 616፣ ኬቢ 665፣ *ሂፊል ተጓዳኝ*
   ለ. ቢወራም – ቢዲቢ 180፣ ኬቢ 210፣ *ፔል ተጓዳኝ*

**40፡5** ይህ ቁጥር የሚያንጸባርቀው የያህዌን ታላቅ የማዳን ድርጊት ነው ለእስራኤል፣ በተለይም ዘጸአት። "እኛ" የሚለው ማመልከት የሚኖርበት የእምነት ማኅበረሰብን ነው፣ ከአብርሃም ዘር (ዘፍ. 12፡1-3)። በኪዳን ማኅበረሰቡ ውስጥ የታመኑትና ያልታመኑት ይገኛሉ (ዝከ. 40፡4)፣ ያህዌም ሁሉንም ማኅበረሰብ ይደግፋል። እሱም ሁለንተናዊ የመዋጀት ዓላማ ለእስራኤል አለው (መዝ. 33:10-12)።

"ተአምራት" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 810፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9፡1 ላይ) ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ከዘጸአት ጋር በተያያዘ ነው።

1. ግሥ – ዘጸ. 3:20፤ 34:10፤ ዘዳ. 28:59
2. ስም – ዘጸ. 15:11

ዘጸአት ዋነኛው ማስረጃ ነበር፣ ያህዌ ለተስፋው ላለው ታማኝነት (ዘፍ. 15፡12-21) እና ለእስራኤል ኃይሉንና ዓላማውን ያሳየበት (ዘፍ. 12፡3)።

◘ **"ከቁጥር ሁሉ በዛ"** ይህ ምናልባት አህዛዊ ትስስር ይሆናል፣ ለአብርሃም የተሰጠው ተስፋ፣ ዘሮቹ ከቁጥር በላይ እንደሚሆኑ (ማለትም፣ እንደ ትቢያ፣ ዘፍ. 13፡16፤ 28፡14፤ ዘኍ. 23፡10፤ እንደ አሸዋ፣ ዘፍ. 22፡17፤ 32፡12፤ እንደ ከዋክብት፣ ዘፍ. 15፡5፤ 22፡17፤ 26፡4)። ሌላው የያህዌ ተአምር፣ ከመሐን፣ ያረጁ ጥንዶች!

የተሻለ ትይዩ ጽሑፍ ሊሆን የሚችለው መዝ. 139፡17-18 ሲሆን፣ እሱም ደግሞ በርካታ የያህዌን የማዳን ሥራ ያሳያል። "እንደ ምድር አሸዋ የሆነ" በሚል የተጠቀሰውን ተገንዘብ፣ እሱም ሌለኛው ጠቃሽ የሆነ ለአብርሃም ዘሮች ለተሰጠው ተስፋ።

**መዝሙር ፡ 40፡6-8**

**[6]መሥዋዕትንና ቍርባንን አልወደድህም**
**ሥጋን አዘጋጀህልኝ**
**የሚቃጠለውንና ስለ ኃጢአት የሚቀርበውን መሥዋዕት አልሻህም።**
**[7]በዚያን ጊዜ አልሁ። እነሆ፥ መጣሁ**
**ስለ እኔ በመጽሐፍ ራስ ተጽፎአል**
**[8]አምላኬ ሆይ፥ ፈቃድህን ለማድረግ ወደድሁ፥**
**ሕግህም በልቤ ውስጥ ነው።**

**40፡6-8** ይህ አንጓ የሙሴን ሕግ ይጠቀማል እንደ ጽሑፋዊ ማሳያ፣ ለመዝሙረኛው አዲስ ግላዊ ግንኙነት፣ ከአዲስ ኪዳን ጋር ተመሳሳይ በሆነ ጽንሰ-ሐሳብ፣ የኤር. 31፡31-34 (ማለትም፣ ሕግህ በልቤ ውስጥ ነው፣ ኢሳ. 51፡7)። ለአምልኮ፣ ለመታዘዝ፣ ለአገልግሎት፣ እና ለመጽናት ያለው ተነሣሽነት ውስጣዊ ነው (ዘዳ. 6፡6)።

መሥዋዕታዊው ሥርዓት ያህዌ ከሰው ኃጢአት ጋር ያለውን የሚይዝበት ዘዴ ነው፣ ከኪዳኑ ማኅበረሰብ ጋር። ንጹሕ የሆኑት እንስሳት ይሞታሉ፣ በኃጢአተኛ ሰው ምትክ (ሕዝ. 18፡4፣20፤ ሮሜ. 6፡23)። እሱም ዐቢይ-ምድባዊ ማሳያ ነው፣ የሚመጣው የእግዚአብሔር በግ፣ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግደው (ዮሐንስ 1፡29፤ ማርቆስ 10፡45፤ 2 ቆሮ. 5፡21፤ ዕብ. 10፡1-18)።

የሙሴ ኪዳን ችግሩ ለብዙዎቹ አይሁድ ውጫዊ የሞራል ሕግ መሆኑ ነው፣ ከቀረበ ግላዊ እምነት አግባብ ይልቅ (ዘዳ. 10፡16፤ 30፡6፤ ኤር. 4፡4፤ 9፡25፤ ሮሜ. 2፡28-29)።

አኪ. ይሄንን አንጓ የሚመለከተው (ቁ. 6-8) በመጨረሻ በኢየሱስ ሕይወትና ሞት እንደተፈጸመ ነው (ዕብ. 10፡5-7 ከLXX)። እሱ ፍጹም ተፍጻሜት ነው የእነዚህ ጽሑፎች። እሱ "ሁነኛው እስራኤላዊ" ነው፣ ለሁሉም ምትክ የሞተ (ኢሳይያስ 53)።

**40፡6** አራት የተለያዩ ቃላት አሉ የእስራኤልን የተለያዩ መሥዋዕት የሚገልጹ (ሌዋውያን 1-7)።

1. መሥዋዕት — ቢዲቢ 257፣ ለመሥዋዕት አጠቃላይ ቃል፣ እዚያም የእንሰሳው ከፊል አካል በኅብረት የሚበላ፣ ከመለኮታቸው ጋር
2. የመብል ቍርባን — ቢዲቢ 585፣ በዋነኛነት ሁለቱንም ነው የሚያመለክተው፣ የእንስሳና የእህል ቁርባን፣ ነገር ግን ለእህል ቍርባን ብቻ ጥቅም ላይ እየዋለ የመጣ
3. የሚቃጠል መሥዋዕት — ቢዲቢ 750 II፣ የሚጠቅሰው በመሠዊያው ላይ ሙሉ ለሙሉ የሚቃጠል መሥዋዕት ነው
4. የኃጢአት መሥዋዕት – ቢዲቢ 308፣ ከሁለቱ ሴቴ ስሞች አንደኛው፤ ይህ የአልፎ አልፎ ነው፣ እሱም "ታላቅ ኃጢአት" በሚል ተተርጉሟል፣ ዘፍ. 20፡9፤ ዘጸ. 32፡21፣30፣31፤ 2 ነገ. 17፡21፤ እና "ኃጢአት" መዝ. 32፡1፤ 109፡7 ላይ። እዚህ እሱ የሚጠቅሰው የኃጢአት መሥዋዕትን ነው፣ ከትይዩነት የተነሣ፣ ነገር ግን አጠቃቀሙ የተለየ ነው።

ይህ ቁጥር መሥዋዕታዊውን ሥርዓት አለመቀበል አይደለም ነገር ግን የተዛባ አጠቃቀሙን እንጂ (1 ሳሙ.15፡22፤ መዝ. 50፡8-14፤ 51፡16-17፤ 69፡30-31፤ ኢሳ. 1፡11-15፤ ኤር. 7፡22-23፤ ሆሴዕ 6፡6፤ አሞጽ 5፡21-22)።

◘

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ተከፍቷል"** |
| **አአመመቅ ኅዳግ** | **"ተቆፍሯል ወይም ተቀዷል"** |
| **አየተመት ኅዳግ** | **"ተቆፍሯል"** |
| **LXX** | **"ያዘጋጀህልኝ ሥጋ"** |

ግሡ (ቢዲቢ 500፣ ኬቢ 496፣ ቃል የተጠናቀቀ) ይህ ፍች የሚኖረው እዚህጋ ብቻ ነው። ለመቆፈር ነው ጥቅም ላይ የዋለው

1. ጉድጓድ – ዘፍ. 26፡25፤ ዘኍ. 21፡18
2. መቃብር – ዘፍ. 50፡5
3. ጉድጓድt – ዘጸ. 21፡23
4. በዘይቤነት፣ ሴራ – መዝ. 7፡16፤ 57፡7፤ 119፡85፤ መዝ. 16፡27፤ 26፡27፤ ኤር. 18፡20 (ማለትም፣ ከኤር. 6፡10 ጋር አነጻጽር)

የአአመመቅ ኅዳግ የሚለው "መውጋት" ነው፣ እሱም ከዘጸ. 21፡5-6 ወይም ዘዳ. 15፡12-18 የመጣ ሊሆን የሚችል፣ እዚያም ባርያው ቋሚ የቤተሰቡ አባል የሚሆንበት (ዝከ. 40፡17፣ የተለየ ግሥ እና "ጆሮ" ነጠላ ነው)።

የLXX ትርጉም የተመሠረተው በተለያዩ የዕብራይስጥ የእጅ ጽሑፎች ላይ ወይም እሱ የ"ጆሮ"ን አስተሳሰብ የጻፈው ለሙሉ አካል እንደ ቆመ አድርጎ ነው። LXX የጥንቷ ቤተ-ክርስቲያን የምትጠቀምበት ነው፣ እናም እሱ ዕብ. 10፡5 (ዕብ. 10፡1-18 ላይ ተጠቅሷል)።

ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ግሡ የሚያመለክተው አዲሱን የእምነትና የመታመን ግንኙነት ነው፣ በአዲሱ ኪዳን ሞዴል የተመሠረተውን (ማለትም፣ "ሕግህ በልቤ ነው፣" ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝ. 36፡26-27)፣ እሱም ኃጢአተኞች ሰዎች የያህዌን ፍቃድ በግልጽ አውቀው እንዲያደርጉ የሚፈቅድ (ማለትም፣ 40፡8)።

**40፡7**

**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"እነሆ፣ መጣሁ"**

**አየተመት፣ አእቅ፣**

**የተእመቅ** **"እለሁ"**
**አኢመቅ** **"እለሁ፣ መጥቻለሁ"**
**LXX** **"እዩ፣ መጥቻለሁ"**
**አእት** **"እዩ፣ መጣሁ"**

"እዚህ አለሁ" የሚለው ትርጉም የመጣው ከተመሳሳይ የመስተጻምር አጠቃቀም ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 243) በኢሳይያስ ጥቅም ላይ የዋለ ኢሳ. 6፡8 ላይ፣ *"መጣሁ"* ከሚለው *ግሥ ጋር* በመደባለቅ (ቢ.ዲ.ቢ. 97፣ ኬቢ 112፣ ቃል የተጠናቀቀ)፣ ከኢሳ. 6፡8 የተለየ *ግሥ*።

እሱም ያህዌ ለአንዱ ሕይወት ላለው ፍቃድና ዕቅድ መገኘትና መማረክ ፈሊጥ ነው (ዝከ. 40፡7ለ-8)። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ (ማለትም፣ *መሥዋዕት*) እሱም የሚያመለክተው ሐቅ፣ በብኪ ምንም ዓይነት መሥዋዕት አለመኖሩን ነው፣ ለሚታወቅ፣ ሆን ተብሎ ለተደረገ ኃጢአት (ሌዋ. 4፡2፣22፣27፤ 5፡15-18፤ 22፡14፤ መዝ. 51፡16-17)። የስሜት ወይም ያለማወቅ ኃጢአት ብቻ ነበር የሚሸፈኑት (ማለትም፣ ሆን ተብለው ያልተደረጉ)። መዝሙረኛው የተመለከተው ብቸኛው ተገቢ መሥዋዕት ራሱ መሆኑን ነው (ሮሜ. 12፡1)። ይህም በርግጥ የእግዚአብሔር በግ ንግር (ጥላ) ነው (ዮሐንስ 1፡29) ራሱን ለመስጠት የመጣው (ማርቆስ 10፡45፤ ኢሳይያስ 53)።

◘ **"በመጽሐፍ ጥቅልል"** አንዳንድ ሊቃውንት ይሄንን የሚመለከቱት ያህዌ ለሙሴ የገለጠውን እንደሚያመለክት ነው። ንጉሡ ቅጅው ተሰጥቶታል (ዘዳ. 17፡18-20፤ 1 ነገ. 2፡3፤ 2 ነገ. 11፡12)። መጽሐፍ ቅዱስ "መጽሐፍ(ጻሕፍት)"ን ይጠቀማል፣ ያህዌ ለእያንዳንዱ ሰው ያለውን ዕቅድ ለመግለጽ (መዝ. 139፡1-6፣ 16) ወይም የሰዎች ሁሉ ሕይወት መታሰቢያ፣ አንድ ቀን በእርሱ ፊት እንደ ዳኛ የሚቆሙ። ይህ ምናብ በሁለት መጻሕፍት ላይ ይገለጻል፣ የሕይወት መጽሐፍ እና የድርጊት መጽሐፍ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሁለቱ መጻሕፍት መዝ. 9፡5 ላይ።

**40፡8 "ፍቃድህን ለማድረግ ወደድሁ"** እንዴት ያለው ሥር-ነቀል ለውጥ ነው፣ ከዘፍጥረት 3። የተጎዳው "የእግዚአብሔር መልክ" ተመልሷል! ኅብረት በጠለቀ ደረጃ ተመልሶ ተችሏል። የውድቀቱ እንደፈለገው የሚሆነው መንፈስ፣ በሚገዛው መንፈስ ተተክቷል።

ኢየሱስ ይሄንን የአገልጋይነት ዝንባሌ ማሳያ ሆኗል፣ እኛ እንድንመለከተው (ማቴ. 26፡39፤ ዮሐንስ 4፡34፤ 5፡30፤ 6፡38)።

## *መዝሙር* ፡ 40፡9-10

**9 በታላቅ ጉባኤ ጽድቅን አወራሁ**
**እነሆ፥ ከንፈሮቼን አልከለክልም**
**አቤቱ፥ አንተ ጽድቄን ታውቃለህ።**
**10 እውነትህንም በልቤ ውስጥ አልሰወርሁም፥**
***ማዳንህንም* ተናገርሁ**
**ምሕረትህንና እውነትህን ከታላቅ ጉባኤ አልሰወርሁም።**

**40፡9-10** መዝሙረኛው የያህዌን ሥራ ይመሰክራል፣ በመቅደስ/በማደሪያው ድንኳን (መዝ. 22፡25) በአምልኮ መቼት (ማለትም፣ ታላቅ ጉባኤ)።

1. ጽድቅህ – ቢ.ዲ.ቢ. 842፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡5 ላይ
2. ታማኝነትህ – ቢ.ዲ.ቢ. 53፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ.. 12፡1 ላይ
3. ማዳንህ – ቢ.ዲ.ቢ. 448፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 13፡5-6
4. ቸርነትህ – ቢ.ዲ.ቢ. 338፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7
5. እውነትህ – ቢ.ዲ.ቢ. 54፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 12፡1 ላይ

ቁጥር 11 እዚህ ዝርዝር ላይ የሚጨምረው አለ (የአንጓ ምድቡ ርግጠኝነት የለውም).

6. ርኅራኄህ – ቢ.ዲ.ቢ. 933
7. ቸርነትህ – ቢ.ዲ.ቢ. 338
8. መታመንህ – ቢ.ዲ.ቢ. 54

እነዚህ ታላላቅ ሥነ-መለኮታዊ የብኪ ቃላት ናቸው፣ ይኸውም የኪዳን አምላክ ከአዳም ወንዶች ልጆች/ሴቶች ልጆች ጋር እንዴት እንደሚሠራ የሚገልጹ፣ በእርሱ የአብርሃም የተለየ መጠራት ምክንያት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)።

**49፡9 "አንተ ታውቃለህ"** ያህዌ የእርሱን ሰብዓዊ ፍጡር ልብ ያውቃል (ኢያ. 22፡22፤ 1 ሳሙ.2፡3፤ 16፡7፤ 1 ነገ. 8፡39፤ 1 ዜና. 28፡9፤ መዝ. 139፡2-4፤ ኤር. 17፡10፤ 20፡12፤ ሉቃስ 16፡15፤ ሐዋ. 1፡24፤ 15፡8፤ ሮሜ. 8፡27)።

**40፡7** እነዚህ ተለጣጣቂ ግሦች፣ መዝሙረኛው የሚያስረግጣቸው የእርሱ ምሉዕና ግልጽ ምስክርነቶች ናቸው፣ ስለ ያህዌ።

1. ተናገርሁ – ቢ.ዲ.ቢ. 142፣ ኬቢ 163፣ *ፔል* የተጠናቀቀ፣ ቁ. 9
2. አልሰወርሁም – ቢ.ዲ.ቢ. 491፣ ኬቢ 487፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ቁ. 10
3. ገለጽኩ – ቢ.ዲ.ቢ. 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ቁ. 10
4. አልሸሸግሁም – ቢ.ዲ.ቢ. 470፣ ኬቢ 469፣ *ፔል* የተጠናቀቀ

ያህዌ ይሻል፣ ሕዝቡ ባሕርዩንና ድርጊቶቹን በምስጋናና በምስክርነት ከፍ ያደርጉ ዘንድ፣ ስለዚህም ሰዎች ሁሉ በአምሳሉ የተፈጠሩት ሰዎች (ዘፍ. 1፡26-27) እሱን አውቀው ያመልኩት ዘንድ!

## *መዝሙር* ፡ 40፡11-12

**11 አቤቱ፥ አንተ ምሕረትህን ከእኔ አታርቅ**
**ቸርነትህና እውነትህ ዘወትር ይጠብቁኝ።**
**12 ቍጥር የሌላት ክፋት አግኝታኛለችና**

**ኃጢአቶቼ ያዙኝ፥ ማየትም ተሳነኝል**
**ከራሴ ጠጕር ይልቅ በዙ፥**
**ልቤም ተወኝ።**

**40፡11-12** ይህ አንጓ የመዝሙረኛውን ወቅታዊ ሁኔታ ይገልጻል። ያህዌ በርግጥ ከእርሱ ጋር ነው፣ ነገር ግን ችግሮች አሉ (ተለጣጣቂ የተጠናቀቁዎች)።

1. ቁጥር የሌላት ክፋት አግኝታኛለችና – ቢዲቢ 67፣ ኬቢ 79፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፤ ይህ ዝርዝር (ኤቢ ገጽ. 247) ምናባዊ ነው፣ ከከባቢ ዱር ውሾች የተወሰደ፣ ሰለባቸውን የሚያጠቁ፤ እነዚህ በርካታ ችግሮች ከያህዌ "ተአምራት" ጋር ተቃርነዋል 40፡5 ላይ
2. ኃጢአቶቼ ያዙኝ – ቢዲቢ 673፣ ኬቢ 727፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ፤ በበርካታ መዝሙራት ላይ በመጽሐፍ አንድ መዝሙረኛው ኃጢአቱን ያምናል፣ ዝከ. 25:11፤ 31:10፤ 32:5፤ 38:4፣18፤ ይህ ጥሬአዊ አገባብ ሊሆን ይችላል የሰዎችን ሁሉ ኃጢአተኝነት ለማስረገጥ
3. ማየትም ተሳነኝል – ቢዲቢ 407፣ ኬቢ 410፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፤ ካለማቋረጥ ማልቀስ ጋር ሊያያዝ ይችላል፣ መዝ. 69፡3፤ ኃጢአት ዘወትር መረበሽን ይፈጥራል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባለን ግንኙነት፣ እንዲሁም የእሱን ፍቃድ የማወቅ ችሎታችንን
4. እሱም በደሉ እጅግ ብዙ መሆኑን ያምናል – ቢዲቢ 782፣ ኬቢ 868፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፤ "የራስ ፀጉር" የሚለው ምስያ መዝ. 69:4 ላይ ተደግሟል፣ እናም በኢየሱስ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ያህዌ እኛን ማወቁን፣ ማቴ. 10:30 ላይ፤ እሱም የብኪ ፈሊጥ ነው፣ 1 ሳሙ.14:45፤ 2 ሳሙ. 14:11፤ 1 ነገ. 1:52፤ ሐዋ 27:34
5. ልቡ ዝሏል (ማለትም፣ ትቶታል) – ቢዲቢ 736፣ ኬቢ 806፣ *ቃል* የተጠናቀቀ

የታማኝ ተከታይ ሕይወት በሚኖር ኃጢአት (ሮሜ 7) እና በእግዚአብሔር ጸጋ እና ምሕረት መካከል የሚሆን ትግል ነው (ሮሜ 8)።

***መዝሙር*** **፡ 40፡13-17**

**13 አቤቱ፥ *ታድነኝ* ዘንድ ፍቀድ**
**አቤቱ፥ እኔን ለመርዳት ፍጠን።**
**14 ነፍሴን ለማጥፋት የሚወድዱ ይፈሩ፥**
**በአንድነትም ይጐስቍሉ**
**በእኔ ላይ ክፋትን ሊያደርጉ የሚወድዱ**
**ወደ ኋላቸው ይመለሱ ይጐስቍሉም።**
**15 እሰይ እሰይ የሚሉኝ**
**እፍረታቸውን ወዲያው ይከፈሉ።**
**16 አቤቱ፥ የሚፈልጉህ ሁሉ በአንተ ደስ ይበላቸው ሐሤትም ያድርጉ**
**ሁልጊዜ ማዳንህን የሚወድዱ**
**ዘወትር። እግዚአብሔር ታላቅ ይሁን ይበሉ።**
**17 እኔ ችግረኛና ምስኪን ነኝ፥**
**ጌታ ግን ያስብልኛል**
**አንተ ረዳቴና መድኃኒቴ ነህ**
**አምላኬ ሆይ፥ አትዘግይ።**

**40፡13-17** እንደተለመደው የማጠቃለያው አንጓ ተለጣጣቂ የጸሎት ጥያቄ ነው (ያልተጠናቀቁዎች እና ተጽዕኗዊዎች በተመሳሳይ ትይዩነት)። ይህ እጅግ ተመሳሳይ ነው ከመዝሙር 70 ጋር።

1. *ታድነኝ* ዘንድ (ቢዲቢ 953፣ ኬቢ 1280፣ *ቃል ተተኳሪ*) ፍቀድ (ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ አወቃቀር). ኤቢ፣ ገጽ. 247፣ የሚለው "ሩጫ" የሚለው *ሥር* አናባቢ መቀየሩን ነው፣ እሱም ቁ. 2ን ትይዩ በመሆን የሚሻል።
2. እኔን ለመርዳት ፍጠን – ቢዲቢ 301፣ ኬቢ 300፣ *ቃል* ተተኳሪ፣ መዝ. 22:19፤ 38:22፤ 70:1፣5፤ 71:12፤ 141:1
3. ነፍሴን ለማጥፋት የሚወድዱ ይፈሩ – ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 35:4፣26፤ 70:2፤ 63:17
4. ነፍሴን ለማጥፋት የሚወድዱ በአንድነት ይፈሩ – ቢዲቢ 344፣ ኬቢ 346፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣
5. በእኔ ላይ ክፋትን ሊያደርጉ የሚወድዱ ወደ ኋላቸው ይመለሱ – ቢዲቢ 690፣ ኬቢ 744፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 35:4፣26፤ 70:2 (ይህ የወታደራዊ ምስያ ነው)
6. በጉዳቴ የሚደሰቱ ይዋረዱ – ቢዲቢ 483፣ ኬቢ 480፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣
7. "እሰይ እሰይ" የሚሉኝ (መዝ. 35:21፤ 70:3) ይፈሩ – ቢዲቢ 1030፣ ኬቢ 1563፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣

40:16 ላይ ጸሎቱ ከአሉታዊ ወደ አዎንታዊ ይቀየራል

8. አንተን የሚፈልጉ ሁሉ ደስ ይበላቸው – ቢዲቢ 965፣ ኬቢ 1314፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ (ኃጢአተኞች ነፍሱን "እንደሚፈልጉ" ተገንዘብ [ቢዲቢ 134፣ ኬቢ 152] መዝሙረኛው ግን ያህዌን ይፈልጋል፣ ዝከ. ቁ. 16)
9. እንተን የሚፈልጉ ሁሉ ደስ ይበላቸው – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣
10. ማዳንህን የሚወድዱ ይበሉ. . . – ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ (የታመኑ ተከታዮች ያህዌን ይወድዳሉ፣ ለእርሱ የተገለጠ ፍቃድና መንገድ ታዛዥ በመሆን። ዘዳ. 6:5፤ 10:12፤ 11:1፣13፣22፤ 19:9፤ 30:15፣16፣ 19-20)

11. “. . .እግዚአብሔር ታላቅ ይሁን” – ቢዲቢ 152፣ ኬቢ 178፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ (ይህ ተቃራኒ ነው፣ ኃጢአተኛው ቁ. 15 ላይ ካለው)
12. ጌታ ግን ያስብልኛል – ቢዲቢ 362፣ ኬቢ 359፣ *ቃል* ተጽዕኗዊ
13. አትዘግይ – ቢዲቢ 29፣ ኬቢ 34፣ *ፔል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ዝከ. 70:5፤ ይህም *ይካተተ (inclusio)* ያበጃል “ፍጠን” ከሚለው ጋር የቁ. 13

**40:17** መዝሙረኛው የራሱንና የያህዌን ባሕርይ እንደሚገልጽ ተገንዘብ።

1. የራሱ
   ሀ. መከረኝነቱን (ቢዲቢ 776)
   ለ. ችግረኝነቱን (ቢዲቢ 2)
   (እነዚህ ዘወትር ለታማኝ ተከታዮች ጥቅም ላይ ይውላሉ፣ መዝ. 70:5፤ 86:1፤ 109:22፤ እዚህጋ ዘይቤአዊ ናቸው፣ ለመንፈሳዊ ፍላጎት፣ ማቴ. 5:3-6)
2. ያህዌ (ኤምቲ አዶን አለው፣ የዕብራይስጥ ኤምኤስኤስ ግን ያህዌ አለው)
   ሀ. የእርሱ ርዳታ (ቢዲቢ 740 I)
   ለ. የእርሱ አዳኝ (ቢዲቢ 812፣ ኬቢ 930፣ *ፔል* አንቀጽ)

▣ **“አምላኬ ሆይ”** በዚህ መዝሙር ላይ ያህዌና ኤሎሂም ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላሉ ይደባለቃሉም፣ 40፡5 ላይ።

1. ያህዌ፣ ቁ. 1፣3፣4፣9፣11፣13 (ሁለቴ)፣16
2. ኤሎሂም፣ ቁ. 3፣5፣8፣17

ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 1:1 ላይ፣ የብኪ ጸሐፍት እነዚህን መጠሪያዎች/ማዕርጎች/ስሞች ለመለኮት እንዴት እንደሚጠቀሙባቸው የተብራራ መግለጫ ለማግኘት፣ የእርሱን ባሕርይና ድርጊቶች የተለያዩ ገጽታዎች ለማስረገጥ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>*መመሪያ*</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የቁጥር 1-10 ሁኔታን (ድባብ) ግለጽ፤ ከዚያም የቁጥር 11-17። ምን ተለወጠ?
2. የያህዌን አስተዋጽዖ ቁጥር 10-11 ዘርዝረህ አብራራ።
3. የመራመድ ምስያ የእምነት ሕይወትን ለመግለጽ እንዴት ጥቅም ላይ ዋለ?
4. ቁጥር 5 የሚጠቅሰው ዘፍጥረትን ነው ወይስ ዘጸአትን፣ ወይስ ሁለቱንም?
5. የLXX ትርጉም የቁ. 6ለ (ዕብ. 10፡5-7) ከኤምቲ እጅግ ልዩነት እንዴት ሊኖረው ቻለ?
6. ይህ መሢሐዊ መዝሙር ነውን?
7. ስለ ምን “መጽሐፍ” ወይም “ጥቅል” ነው ቁጥር 7ለ የሚናገረው?
8. ቁጥር 13-17 ዳግም መዝሙር 70 ላይ ለምን ይከሰታል?

## መዝሙር 41
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| *መዝሙረኛው በሕመም ላይ ስለ ጠላቶችና ሐሰተኛ ጓደኞች ሲመረር*<br><br>*ኤምቲ መግቢያ “ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር”* | *የመልካሞች ባርኮትና መከራ* | *ከበሽታ ለመፈወስ ጸሎት (ኀዘን)* | *ጸሎት በሕመም ጊዜ* | *የመከረኛና የብቸኛ ጸሎት* |
| 41:1-3<br>41:4-9<br>41:10-12<br>41:13 | 41:1-3<br>41:4-6<br>41:7-9<br>41:10-12<br>41:13 | 41:1-3<br>41:4-10<br>41:11-12<br>41:13 | 41:1-3<br>41:4-9<br>41:10-13 | 41:1-3<br>41:4-9<br>41:10-12<br>41:13 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (**ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል**)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 41፡1-3**
**1ለችግረኛና ለምስኪን የሚያስብ ምስጉን ነው**
**እግዚአብሔር በክፉ ቀን ያድነዋል።**
**2እግዚአብሔር ይጠብቀዋል፥ ሕያውም ያደርገዋል፥**
**በምድር ላይም ያስመሰግነዋል፥**
**በጠላቶቹም እጅ አያሳልፈውም።**
**3እግዚአብሔር በደዌው አልጋ ሳለ ይረዳዋል**
**መኝታውን ሁሉ በበሽታው ጊዜ ያነጥፍለታል።**

**41፡1-3** ይህ ቀዳሚ አንጓ ባርኮቶችን ይገልጻል (ቢ.ዲ.ቢ. 80፣ መዝ. 1፡1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት) የሙሴን ሕግ ለሚጠብቅ ሰው፣ እሱም እስራኤል ደግ፣ ደጋፊ፣ እና ለተቸገሩት የሚረዳ እንዲሆን የሚጠይቅ (ቢ.ዲ.ቢ 195፣ ዘጸ. 23:5፤ ሌዋ. 14:21፤ መዝ. 72:13፤ 82:3፤ 113:7፤ ምሳ. 19:17፤ 21:13፤ 28:3፣8፤ 29:7፣14)። እነርሱን የሚረዱ፣ በተጨባጭ አምላካቸውን እየረዱ ነው (ኢየሱስ ስለመጨረሻው ፍርድ ማቴ. 25፡31-46 ላይ ተረናገረውን ተመልከት)።

በዚህ ቃል የተገለጹት ሰዎች ዓይነት።

1. መበለቶች (ባል የሞተባቸው ሴቶች) (ዘጸ. 22:22፤ ዘዳ. 10:18፤ 24:17-18፤ 27:19፤ መዝ. 68:5)
2. ደሀ-አደጎች (የሙት ልጆች)
3. ባዕዳን (የሰው ሀገር ሰዎች) (ሌዋ. 19:33-34፤ ዘጸ. 22:21-22፤ ዘዳ. 24:17-18፤ 27:19)
4. ዓይነ-ስውር/ሸባ

5. በማኅበረሰቡ ደካሞች የሆኑ (ርስት የሌላቸው)
6. ችግረኞች (ለሕይወት መሠረታዊ ነገር የሌላቸው — ምግብ፣ መጠለያ፣ ሥራ፣ ወዘተ...)

ለታዛዥ የኪዳን ተከታይ ያህዌ ምን እንደሚያደርግ ተገንዘብ (ደህን መርዳት አንድ ነገር ነው፣ ነገር ግን እዚህ ለሙሉው ሕግ ቆሟል)።

1. ያህዌ በክፉ ቀን ያድነዋል
2. ያህዌ ይጠብቀዋል
3. ያህዌ በሕይወት ያኖረዋል
4. "ብፁዕ" (የተባረከ) ተብሎ ይጠራል (ኤምቲ ያልተጠናቀቀ አለው ነገር ግን ማሶረቲካዊ ሊቃውንት የሚያስቡት የተጠናቀቀው ከዋው ጋር የተሻለ እንደሆነ ነው፤ ፍችው አይቀየርም)
5. ያህዌ ለጠላቶቹ አሳልፎ አይሰጠውም
6. ያህዌ በሕመሙ ጊዜ ይደግፈዋል
7. ያህዌ ጤናውን ይመልስለታል

ሁሉም ያልተጠናቀቁ ግሦች የሚገልጹት የእግዚአብሔርን ቀጣይነት ያለው ድርጊት ነው፣ በሕይወት ሁሉ ውስጥ።

ይሄንን የመሰሉትን አጠቃላይ መግለጫዎች በጥበብ ሥነ-ጽሑፍ ላይ ተገንዘብ። ይህም እንደ ተስፋ ተደርጎ መወሰድ አይኖርበትም፣ ሁሉንም ሰው፣ ሁልጊዜ እንደሚመለከት፣ ደህን የሚረዳውን። ይህ አጠቃላይ መግለጫ ነው። ይህም አብዛኛውን ጊዜ እውነት ነው፣ ነገር ግን በእያንዳንዱና በሁሉም ጊዜ አይሆንም። የምንኖረው በወደቀው ዓለም ነው!

ይህ የማቴዎስ 7 የተሻለ መግለጫ ነው። አንዱ ሕይወቱን እንዴት እንደሚኖር፣ እንዴት እንደሚናገር፣ ሀብቱንና ጊዜውን እንዴት እንደሚመድብ፣ የልቡን ቀዳሚ ትኩረት ይገልጣል!

**41፡2 "በምድር ላይ"** የዕብራይስጡ ቃል "መሬት" (ቢዲቢ 75) ሊል የሚችለው

1. መስክ
2. ሁዳድ (ቀበሌ)
3. አገር
4. ስፍራ
5. ዓለም ነው

ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡2 ላይ። ዐውደ-ጽሑፍ ብቻ ነው ሊናገር የሚችለው። እኔ ማመን ችያለሁ በቤርናርድ ራም፣ *ክርስቲያናዊ አተያይ የሳይንስ እና ቅዱስ ቃሉ* ማለትም የዘፍጥረት 6-9 የጥፋት ውኃ ካባቢያዊ ነበር፣ ከዚህ ቃል አጠቃቀም የተነሣ፣ በዚያ ዐውደ-ጽሑፍ። የእኔን ኮሜንተሪ (ሐተታ) ተመልከት በዘፍጥረት 1-11 ላይ በነጻ የዌብ ሳይት መስመር www.freebiblecommentary.org።

**መዝሙር ፡ 41፡4-9**

**4እኔስ። አቤቱ ማረኝ**
**አንተን በድያለሁና ነፍሴን ፈውሳት አልሁ።**
**5ጠላቶቼም በላዬ ክፋትን ይናገራሉ።**
**መቼ ይሞታል ስሙስ መቼ ይሻራል? ይላሉ።**
**6እኔን ለማየት ቢገባ ከንቱን ይናገራል**
**ልቡ ኃጢአትን ሰበሰበለት**
**ወደ ሜዳ ይወጣል ይናገራልም።**
**7በላዬ በመተባበር ጠላቶቼ ሁሉ ይሾካሾኩብኛል፥**
**በእኔ ላይም ክፋትን ያስባሉ።**
**8ክፉ ነገር መጣበት**
**ተኝቶአል ከእንግዲህ ወዲህ አይነሣም ይላሉ።**
**9ደግሞ የሰላሜ ሰው የታመንሁበት**
**እንጀራዬን የበላ**
**በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ።**

**41፡4-9** የእነዚህ አንጓዎች ሎጂካዊ ግንኙነት አልተመለከተም። ሊሆን የሚችለው፣ ደራሲው ቁጥር 1-3 እንደተገለጸው ዓይነት ሰው ነው፣ ነገር ግን ሕይወቱ በመከራ ውስጥ ነው፣ ከሌሎች በተሰነዘረበት ጥቃት ሳቢያ። በግልጽ እንደሚታየው፣ ኃጢአት መሥራቱን ተቀብሏል (ቁ. 4)። አብዛኞቹ የመጽሐፍ 1 የመጨረሻዎቹ መዝሙራት (መዝሙር 1-41) የኃጢአትን ንስሐ ወይም እውቂያ ይጠቅሳሉ።

በርካታ ችግሮች ተጠቅሰዋል።

1. እሱ በአካሉና በመንፈሱ ታሟል
2. ጠላቶች አሉት የሚሰድቡት (ስሙን የሚያጠፉት) (ቁ. 5-7)
3. እነርሱም በእርሱ ላይ ክፉ አስበዋል (ቁ. 7-8)
4. ጠላቶቹ በአንድ ጊዜ የቅርብ ባልንጀሮቹ ነበሩ (ቁ. 9፤ መዝ. 35፡11-16፤ 55፡12-13፣20)። ይህም ዮሐንስ 13፡18 ላይ ተጠቅሷል፣ ስለ ይሁዳ ኢየሱስን መካድ።

**41፡7 "ይንሾካሾኩብኛል"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 538፣ ኬቢ 527፣ *ሂዝፔል ያልተጠናቀቀ*) ለርግማን/ምርቃት ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል (መዝ. 58፡5፤ መክ. 10፡11፤ ኢሳ. 3፡2-3) ወይም እሱ ዝግ ባለ ድምጽ የሚናገሩ ሰዎችን ሊሆን ይችላል እንዳይሰሙ (2 ሳሙ. 12፡19) ወይም ዝቅ ያለ ድምጽ፣ በጸሎት ላይ (ኢሳ. 26፡16)።

በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ላይ ርግማንን የሚጠቅስ ከሆነ፣ ቁጥር 8 ውጤቱ ነው።

**41:8**
**አአመመቅ** **"ከፉ ነገር በላዩ ፈሰሰ"**
**አኪጀት** **"ከፉ ሕመም፣ አሉ እንርሱ፣ ይዞታል"**
**አየተመት** **"እነርሱ አሰቡ፣ ገዳይ ነገር ተጣብቆታል"**
**አእቅ** **"እነርሱ አሉ፣ በገዳይ በሽታ ታሟል'"**
**አኢመቅ** **"ገዳይ በሽታ ግዞታል"**
**የተእመቅ** **"ከፉ ነገር ወርዶበታል፣ አሉ እነርሱ"**

"ከፉ" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 116) ኋላ ላይ *ቢልአል* የሚለውን መጠሪያ (ዘዳ. 13:13፤ 2 ቆሮ. 6:15)። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው በበርካታ መልኩ ነው፣ የተሻለ ምሳሌ የሚሆነው 1 ሳሙ.1:16፤ 2:12፤ 25:17።

አጠቃቀሙ እዚህጋ የሚመስለው የሕመም ሰውኛ ዘይቤ ነው፣ እነርሱ እንደሚመለከቱት ከያህዌ የተላከ፣ በመዝሙረኛው ኃጢአት ምክንያት (የኢዮብ ሦስቱ ባልንጀሮች)። ለእርሱ የያህዌ ድርጊቶች ግን 41፡10-12 ላይ የሚያሳየው የእነርሱ አባባል ሐሰት/ስም ማጥፋት እንደሆነ ነው።

**41፡9 "በእኔ ላይ ተረከዙን አነሣ"** ይህ ባህላዊ የማግለል ድርጊት (ትይዩ ምንባብ አለመኖሩን ተገንዘብ) የመጣው ከአንድነት/ኪዳን ሙብል በኋላ ነው (ዘፍ. 26:28-30፤ 31:51-54፤ ዘጸ. 12:18፤ 24:5፤ መዝ. 69:23)።

ይህንንም መመልከት የሚቻለው እንደ

1. የተንኮል/የዓመጽ ድርጊት ነው፣ በመዝሙረኛው ላይ (ማለትም፣ በእግር መደፍጠጥ)
2. የስድብ ድርጊት፣ በሰውነት አካል የሚገለጽ። በመካከለኛው ምስራቅ አሁንም ቢሆን ብርቱ ስድብ ነው፣ አንዱ ከጫማ በታች መሆኑን ለማሳየት።

ንቀት ማሳየቱ እጅግ የሚነካ ነው በሁለቱ መካከል ካለው ግልጽ የሆነ ወዳጅነት የተነሣ።

▣ **"የቅርብ ወዳጄ"** ይህ በጥሬው "የሰላሜ ሰው ተቀይሮ የቢልያል (ከፉ) ልጅ የሆነ" ማለት ነው (ቁ. 8ሀ)።

---

**መዝሙር ፡ 41፡10-12**

**[10]አንተ ግን አቤቱ፥ ማረኝ**
**እመልስላቸውም ዘንድ አስነሣኝ።**
**[11]ጠላቴ እልል አይልብኝምና**
**ስለዚህ እንደ ወደድኸኝ አወቅሁ።**
**[12]እኔን ግን ስለ ቅንነቴ ተቀበልኸኝ፥**
**በፊትህም ለዘላለም አጸናኸኝ።**

---

**41፡10-12** ቁጥር 4 ላይ ሁለት ጥያቄዎች ነበሩ (ተተኳሪዎች)።

1. ማረኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 335፣ ኬቢ. 334፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. ነፍሴን ፈውስ (*ኔፍሽ፡ መዝ.* 3:2 ላይ ማስታወሻ ተመልከት) – ቢ.ዲ.ቢ. 950፣ ኬቢ. 1272፣ *ቃል ተተኳሪ*

እንግዲህ በቀጣዩ አንጓ ሁለት ተተኳሪዎች እና አንድ ተጓዳኝ አለ።

1. እንደ ላይኛው ቁ. 1 ተመሳሳይ፣ 41:4
2. አነሣኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 877፣ ኬቢ. 1086፣ *ሂፊል ተተኳሪ* (ተመሳሳይ ጥያቄ፣ የተለየ ግን ትይዩ ግሥ ከቁ. 2 ከላይኛው)፣ 41:4
3. እመልስላቸው ዘንድ – ቢ.ዲ.ቢ. 1022፣ ኬቢ. 1532 *ፔል ተጓዳኝ*፤ መዝሙረኛው ይሻል የያህዌ የፍርድ መሣርያ ይሆን ዘንድ

ፈውስ የሚታይ ማስረጃ ይሆናል፣ ያህዌ ጸሎቱን መስማቱንና ምላሽ ለመስጠቱ። እሱም በርግጥ የሚታይ የያህዌ መገለጥ አይደለም መዝሙረኛውን ያስደሰተው፣ ነገር ግን

1. እሱም የያህዌ ደስ መሰኘት ምልክት ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 342፣ ኬቢ. 339፣ *ቃል የተጠናቀቀ*) በእርሱ
2. ያህዌ ደግፎታል (ቢ.ዲ.ቢ. 1069፣ ኬቢ. 1751፣ *ቃል የተጠናቀቀ፣ መዝ.* 63:8) የእርሱን ቅንነት (ቢ.ዲ.ቢ. 1070)። ማለትም ንጽሕናው (መዝ. 25:21፤ 101:2፤ ምሳ. 10:9፤ 19:1፤ 20:7፤ 28:6)
3. ያህዌ አኑሮታል (ቢ.ዲ.ቢ. 662፣ ኬቢ. 714፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ* ከዋው ጋር) በመገኘቱ (ማለትም፣ ማደርያ ድንኳን/መቅደስ፣ መዝ. 16:11፤ 23:6፤ 27:4-6) ለዘላለም (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9:5 ላይ)።

---

**መዝሙር ፡ 41፡13**

**[13]ከዘላለም እስከ ዘላለም**
**የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ።**
**አሜን አሜን**

---

**41፡13** ይህ ውዳሴያዊ የአምልኮ መዝጊያ ነው (መዝ. 72:18-19፤ 89:52፤ 103:19-22፤ 106:48፤ 150:6)። እሱ ምናልባት በመነሻው የመዝሙር 41 አካል ላይሆን ይችላል፣ ነገር ግን የመጀመሪያው መጽሐፍ አጠቃላይ መዝጊያ (መዝሙር 1-41) የመዝሙሩ።

1. መዝሙር 72:18-19 መጽሐፍ IIን ይዘጋል
2. መዝሙር 89:52 መጽሐፍ IIIን ይዘጋል
3. መዝሙር 106:47-48 መጽሐፍ IVን ይዘጋል
4. መዝሙር 150:6 መጽሐፍ Vን ይዘጋል

▣ **"አሜን፣ አሜን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት ከታች ያለውን።

**ልዩ ርዕስ፡ አሜን**

I. ብሉይ ኪዳን

ሀ. "አሜን" የሚለው ቃል የመጣው ከዕብራይስጥ ቃል

1. "እውነት"" (*emeth*፣ BDB 49)
2. "እውነተኛ"(*emun*፣ *emunah*፣ BDB 53)
3. "እምነተ" ወይም " የሚታመን"
4. "ታማኝ"(*dmn*፣ BDB 52)

ለ. የቃሉ ሥረወ ግንድ ምንጭ አካላዊ አለመዋዠቅ ነው፡፡ የዚህ ቃል ተቃራኒ የማይጸና፣ ተንሸራታች (ዘዳ 28፡64-67፤ 38፡16፤ መዝ 40፡ 2፤ 73፡18፤ ኤር 23፡12)፡፡ ከዚህ የቃሉ ቀጥተኛ ትረርጉም ምሳሌያዊ ትርጓሜው ተወስዷል ይኼውም ታማኝነት፣ የሚታመን፣ ሀቀኛ እና የመሳሰሉት ናቸው (ዘፍ 15፡16፣ እንባቆም 2፡4)

ሐ. ልዩ የቃሉ አጠቃቀም

1. አማድ 1 ነገስት 18፡16 (1 ጢሞ 3፡15)
2. ማረጋገጫ ዘጸ 17፡12
3. የማይናወጥ ዘጸ 17፡12
4. የተረጋጋ ኢሳ 33፡6፤ 34፡5-7
5. እውነት 1 ነገ 10፡6፤ 17፡24፤ 22፡16፤ ምሳ 12፡22
6. ጽናት 2 ዜና 20፡20፤ ኢሳ 7፡9
7. የሚታመን መዝ 119፡43፣ 142፣ 151፣ 168

መ. በ ብሉይ ኪዳን ውስጥ የሚሰራ እምነት ለማመልከት ሌላ የዕብራይስጥ ቃል አገልግሎት ላይ ውሏል

1. *bathach* (BDB 105)፣ባታች፣ መታመን ማለት ነው
2. *yra* (BDB 431)፣ ያራ መፍራት፣ ማክበር፣ ማልከም ማለት ነው

ሠ. የዚህ ቃል ሥነ መለኮታዊ እሳቤ የሰው ልጆች ታማኝነት ሳይሆን የያሕዌ ታማኝነት ነው (ዘጸ 34፡6፣ ዘዳ 32፡4፤ መዝ 108፡4፤ 115፡1፤ 117፡2፤ 138፡2)፡፡ የወደቀው የሰው ልጅ ብቸኛ ተስፋ የያሕዌ ምህረት የሞላበት የቃል ኪዳን ታማኝነት እና የእርሱ የተስፋ ቃል ነው፡፡ ያሕዌን የሚያውቁት ሁሉ እንደ እርሱ ልሆኑ ይገባል (ዕባ 2፡4) መጽሐፍ ቅዱስ እግዘኢብሔር በሰው ልጆች ውስጥ መልኩን ለመመለስ የሚያደርገው ጥት ታርክ እና ዘገገባ ነው (ዘፍ 1፡26-27)፡፡ ድነት የሰው ልጆችን ከእግዚአብሔር ጋር የጠበቅ ግንኙነት የማድግ ብቃትን የሚመለስበት ነው፡፡ ለዚህም ነው እኛ የተፈጠርነው፡፡

II. አዲስ ኪዳን

ሀ. "አሜን" የሚለው ቃል የተለያዩ ሀይማታዊ አዎንታዎች ትክክለኝነታቸውን ለማረጋገጥ በአዲስ ኪዳን ውስጥ ብዙ ጊዜ አገልግሎት ላይ ውሏል፡፡ (1ቆሮ 14፡16፣ 2ቆሮ 1፡20፣ ራዕ 1፡7፣ 5፡14፣ 7፡12)

ለ. ይህ ቃል በአዲስ ኪዳን ውስጥ ከጸሎቶች ጋር ተያይዞ ይገኛል (ሮሜ 1፡25፤ 9፡5፤ 11፡36፤ 16፡27፤ ገላ 1፡5፤ 6፡18፤ ኤፌ 321፤ ፊል 4፡ 20፤ 2 ተሰ 3፡18፤ 1ጢሞ 1፡17፤ 6ለ16፤ 2ጢሞ 4፡18)፡፡

ሐ. ይህንን ቃል በጣም ጠቃሚ አረፍተ ነገርን ለመጀመር የተጠቀመበት ኢየሱስ ብቻ ነው (ይህም በዮሐንስ ወንጌል ውስጥ ተከታታይ ሆኖ ተገልጾዋል) (ሉቃ 4፡24፣ 12፡37፤ 18፡17፣ 29፤ 21፡32፤ 23፡43)

መ. በራዕ 3፡14 ላይ የኢየሱስ ማዕረግ ሆኗል (ምናልባትም ከኢሳ 65፡16 የያሕዌ ማዕረግ ሊሆን ይችላል)፡፡

ሠ. የታማኝነት ወይም የእምነት፤ የመታን የሚሉ ቃላት የግሪክ ቃል የሆነው ፒስቶ ወይም ፒስቲስ የሚያመለክቱ ሲሆን ወደ አማርኛ ስተረጎሙ "መታመን"፣ "እምት" ወይም" ማመን" ማለት ነው፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ቁጥር 1ሀ ማንን ነው የሚጠቅሰው?
2. ኃጢአትና ሕመም እንዴት ይዛመዳሉ?
3. ቁጥር 7 የሚመለከተው ሹክሹክታንና ስም ማጥፋትን ነው ወይስ ርግማንና ምርቃትን?
4. "ክፉ ነገሮች" ምንድናቸው፣ ቁጥር 8 ላይ?
5. ቁጥር 9 እንዴት አድርጎ ነው አኪ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው?
   ምንድንስ ነው አንድምታው?
6. መዝሙረኛው ቁጥር 12 ላይ በትክክል የሚያስረግጠው ምንድነው? ምንድነው የፈለገው?
7. ቁጥር 13 የመዝሙሩ ክፍል ያልሆነው ለምንድነው?

## መዝሙር 42
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| አምላክን መታመን፣ በችግርና በስደት<br>ኤምቲ መግቢያ ለመዘምራን አለቃ። የቆሬ ልጆች ትምህርት | እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ፣ በችግር መሐል | የፈውስ ጸሎት፣ ለመከራ በመዘጋጀት ጊዜ | በስደት ላለ ሰው መጸለይ | የሌዋዊ ሰቆቃ በስደት |
| 42:1-4 | | | | |
| | 42:1-3 | 42:1-3 | 42:1-3 | 42:1 |
| | | | | 42:2 |
| | | | | 42:3 |
| 42:5-8 | 42:4 | 42:4-5ለ | 42:4-5 | 42:4 |
| | 42:5 | 42:5ሐ-6ሀ | | 42:5-6ሐ |
| | 42:6-8 | 42:6ለ-8 | 42:6-8 | 42:6ለ-መ |
| | | | | 42:7 |
| 42:9-11 | | | | 42:8 |
| | 42:9-10 | 42:9-10 | 42:9-10 | 42:9 |
| | | | | 42:10 |
| | 42:11 | 42:11 | 42:11 | 42:11 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልስህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. የመጀመሪያው ቁጥር ዘወትር በጥልቀት ነው የሚናገረኝ። ይህ ነው የግላዊ ግንኙነት ዋነኛ ሐሳብ መሆን የሚኖርበት። ነገር ግን ይኸው ጥልቅ ቅርበት እንኳ ቢሆን ችግሮች፣ ሕማም፣ ክፉ ጥቃቶች አይከሰቱም ማለት አይደለም። ታላቁ ተስፋ የችግሮች አለመኖር አይደለም፣ የእርሱ መገኘት እንጂ (መዝ. 23፡4፤ 16፡8)።

ለ. መዝሙረኛው በስደት ላይ እንዳለ አስባለሁ።
1. ወደ መቅደስ መሄድ አልቻለም፣ ቁ. 4
2. ከነአንን ናፍቋል፣ ቁ. 6
3. በማራኪዎቹ ማስፈራራት ደርሶበታል፣ ቁ. 3፣ 10 (መዝሙር 137፣ እሱም ደግሞ የስደት መዝሙር የሆነ)። የአአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 781) ማራኪ ሐሳብ አለው፣ ማለትም መዝሙረኛው ቆሬአዊ ሌዋዊ ለመሆኑ፣ በሶርያ የተማረከ። እሱም ለሶርያ ወረራ አንድ ምሳሌ ይሆናል (ምሳ. 2 ነገ. 12፡17-18)። ቆሬአዊ በእስራኤል ሰሜናዊ ስፍራ ይኖሩ ነበር (ኢያ. 2፡ 4፤9-19)። ይህም ሊያስረዳ የሚችለው
1. የስደት ንድፈ-ሐሳብ
2. ሰሜናዊውን መልክዓ ምድራዊ ስፍራዎች፣ ቁጥር 6 ላይ

ሐ. ተደጋጋሚው ሐረግ "በተስፋ መቁረጥ" ("መጣል፣" ቢዲቢ 1005፣ ኬቢ 1458፣ ሂዝፖለል (ያልተጠናቀቀ) ሦስት ጊዜ ተከስቷል በዚህ በአጭር ግጥም ላይ፣ ቁጥር 5፣ 6፣ እና 11። መዝሙረኛው በውስጥም (ቁ. 5) በውጭም (ቁ. 10) ተጎድቷል።

ደግሞም ቁጥር 5 እና 11 መደገማቸውን ተመልከት፣ በመጠነኛ ለውጦች ብቻ። ይኸው ተመሳሳይ ቁጥር እንደገና በድጋሚ ይከሰታል መዝ. 43፡5 ላይ፣ እነዚህ መዝሙራት በቅርበት መያያዛቸውን የሚያመለክት፣ ምናልባትም አንድ መዝሙር ይሆናሉ (ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ 398)።

# የቃልና የሐረግ ጥናት

***መዝሙር ፡ 42፡1-4***

***[1]ዋላ ወደ ውኃ ምንጭ እንደሚናፍቅ፥***
***አቤቱ፥ እንዲሁ ነፍሴ ወደ አንተ ትናፍቃለች።***
***[2]ነፍሴ ወደ ሕያው አምላክ ተጠማች***
***መቼ እደርሳለሁ? የአምላክንስ ፊት መቼ አያለሁ?***
***[3]ዘወትር። አምላክህ ወዴት ነው? ሲሉኝ***
***እንባዬ በቀንና በሌሊት ምግብ ሆነኝ።***
***[4]ይህን ሳስብ ነፍሴ በእኔ ውስጥ ፈሰሰች፥***
***ወደ እግዚአብሔር ቤት ወደ ምስጋና መኖሪያ ስፍራ እገባለሁና***
***በዓል የሚያደርጉ ሰዎች የደስታና ምስጋና ቃል አሰሙ።***

**42፡1-4** በዚህ አንጓ ላይ አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ችግሩ ምን እንደሆነ።

1. መዝሙረኛው ከእግዚአብሔር እንደተቆረጠ ይሰማዋል
2. መዝሙረኛው በመቅደስ ማምለክ አልቻለም (ዝኪ. ቁ. 4ለ፣ሐ)
3. የመዝሙረኛው እምነት ተሞግቷል፣ አሁን ባለበት ሁኔታ (ማለትም፣ ስደት) በጨቋኞቹ ማስፈራራት (ቁ. 3፣10፤ 79:10፤ 115:2)

ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘትን ተመልከት፣ ለ።

**42:1**

**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"እንደሚናፍቅ"**
**አየተመት፣ አእቅ፣**
**LXX፣ የተእመቅ** **"እንደሚናፍቅ"**
**አኢመቅ** **"እንደሚመኝ"**
**ጄፒኤስአኤ** **"እንደሚጮኽ"**

ይህ ግሥ (ቢዲቢ 788፣ ኬቢ 881፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) ሦስት ጊዜ ብቻ ነው ብኪ ላይ የሚገኘው፣ ሁለቱ እዚህጋ እና አንዴ ኢዩኤል 1፡20 ላይ፣ እሱም ለዱር እንስሳት ጥቅም ላይ የዋለ።

ተርጓሚው የመዝሙረኛው እግዚአብሔርን ጥልቅ መሻት አጽንዖት ነውን (መዝ. 63፡1) ወይስ የእሱን ፍላጎት በመቅደስ በበዓል ቀን ለመሆን (42፡4) ? እንደማስበው ቁ. 2 በተሻለ ከዐውደ-ጽሑፉ ጋር ይገጥማል።

▣ **"ነፍስ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ኔፊሽ ነው (ቢዲቢ 659፣ዝኪ. 42:2፣4፣5፣6፣11)። ማስታወሻ ተመልከት መዝሙር 3፡2 ላይ። እሱም ፈሊጥ ነው ራስን ለመጥቀሻ።

▣ **"ሕያው አምላክ"** ይህ የቃላት መቀያየር ነው

1. ኖረ (ግሥ፣ היה ፣ ቢዲቢ 310)
2. ሕያው ( חי ፣ ቅጽል፣ ቢዲቢ 311 l)
3. ያህዌ (יהוה ፣ ቢዲቢ 217፣ የመለኮት የኪዳን ስም፣ ዘፍ. 2:4፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:1 ላይ)

ያህዌ ነው ብቸኛው ሕያው፣ ዘላለም ኗሪው አምላክ፣ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት (አንድ አምላክ) መዝ. 2፡7 ላይ)። የቀሩት ሁሉ የሚኖሩት በእርሱ፣ ከእርሱ፣ ለእርሱ ነው (መዝ. 18፡46)። ይህ የእስራኤልን አምላክ እንደ "ሕያው" ባሕርይ መስጠት፣ ከጣዖት አምልኮ ጋር ይቃረናል፣ ከዕውር፣ ደንቆሮ፣ እና ሕልውና ከሌላቸው ጋር (ኢሳ. 4:9-20፤ ዕን. 2:18-19)።

**42፡2 "በእግዚአብሔር *ፊት መሆን*"** ይህ ፈሊጥ ነው፣ በበዓል ቀን በመቅደስ ለመሆን። መዝሙረኛው በበዓል ቀን በኢየሩሳሌም እንዳይሆን ተከልክሏል።

ጥያቄ አለ፣ ተናባቢዎቹን እንዴት መረዳት እንደሚቻል።

1. አአመመቅ ኤምቲን ይከተላል፣ "በፊቱ መሆን"
2. የተመት አናባቢዎቹን ይቀይራል "እነሆም የእግዚአብሔር ፊት" በሚል

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 232) ለአማራጭ ቁ. 2 "ሐ" ደረጃ ይሰጣል (ማለትም፣ ተገቢ የሆነ ጥርጣሬ)።

**42፡3 "*እነርሱ*"** ጽሑፉ አልለየም፣ ይህ ማንን እንደሚመለከት።

1. ማራኪዎች
2. ጠላቶች
3. ጣዖት አምላኪዎች

እንደሚመስለኝ ቁ. 1 ከመዝሙሩ ጋር በተሻለ ይገጥማል። አኢመቅ ይሄንን መዝሙር "የሌዋዊ ሰቆቃ በስደት" በሚል ሰይሞታል።

መዝሙረኛው እነዚህ ሰዎች ቀኑን ሁሉ እንደሚያስፈራሩት እንደሚሰማው ተገንዘብ (v. 3b፤ 79:10፤ 115:2)።

**42:4** አምልኮ በደስታ የሚጠበቅ ልምምድ መሆን አለበት። የእናንተም የአምልኮ ጊዜ እንደዚህ ዓይነት ባሕርይ እንደሚኖረው ተስፋ አደርጋለሁ!
*መዝሙረኛው የቀድሞ የአምልኮውን ጊዜ ያስታውሳል።*

1. አስታውሳለሁ – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ *ቃል ተጓዳኝ*
2. ነፍሴን በውስጤ አፈስሳለሁ – ቢዲቢ 1049፣ ኬቢ 1629፣ *ቃል ተጓዳኝ*

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አየተመት** | **"ስብስብ ሕዝብ"** |
| **አኪጀት** | **"ሕዝብ"** |
| **አእቅ፣ ጀፒኤስአኤ** | **"ሕዝብ"** |
| **አኢመቅ** | **"ከጣራ በታች"** |
| **LXX** | **"ድንኳን"** |

*ቃሉ* (ቢዲቢ 697) የሚተረጉመው "ስብስብ ሕዝብ" እዚህጋ ብቻ ነው፣ ብኪጋ የሚገኘው፣ ነገር ግን ተመሳሳይ ተናባቢዎች "ትኬት፣" "ሽፋን፣" "ድንኳን፣" "ዳስ" ሊሉ ይችላሉ። LXX የሁለተኛውን አማራጭ ትይዩነት የሚመለከተው ይህንን ቃል በተሻለ መንገድ እንደሚተረጉም ነው (እጅግ ብዙ፣ ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ማስታወሻ፣ ገጽ 233)። ለተሻለ አጭር ማብራሪያ ኒዶቴ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 247 ተመልከት።

▣ ***"በርጋታ መራቸው"*** በዚህ ቃል ፍች ላይ አንዳንድ ውዥንብር (ግልጽ ያልሆኑ ነገሮች) አሉ።

1. "በዝግታ መራመድ" – ቢዲቢ 186፣ ኬቢ 214፣ *ሂዝፔል* ያልተጠናቀቀ (መዝሙረኛው ቆሬያዊ ሌዋዊ ዘማሪ ነበር፣ በመቅደስ የአምልኮ *ሥርዓት*፣ ዝማሬ፣ እና አምልኮ ላይ የሚሳተፍ፣ 2 ዜና. 20:19)
2. "ባለ ግርማ" — የመገናኛውን ድንኳን የማምለኪያ ስፍራ ያመለክታል (አኢመቅ፣ የተእመቅ)
3. ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 234) "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል (ተገቢ ጥርጣሬ) ለ "መራኋቸው።"

በሦስቱም አማራጮች ላይ ያለው ብቸኛው ልዩነት የአናባቢዎች ምልክት ነው።

## *መዝሙር* : 42:5-8

**[5]ነፍሴ ሆይ፥ ለምን ታዝኛለሽ?**
**ለምንስ ታውኪኛለሽ?**
**የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ**
**በእግዚአብሔር ታመኚ።**
**[6]አምላኬ ሆይ፥ ነፍሴ በእኔ ውስጥ ታወከች**
**ስለዚህ በዮርዳኖስ ምድር**
**በአርሞንኤምም በታናሹ ተራራ አስብሃለሁ።**
**[7]በፍዋፍዋቴህ ድምፅ ቀላይ ቀላይን ትጠራታለች**
**ማዕበልህና ሞገድህ ሁሉ በላዬ አለፈ።**
**[8]እግዚአብሔር በቀን ቸርነቱን ያዝዛል፥**
**በሌሊትም ዝማሬው በእኔ ዘንድ ይሆናል**
**የእኔ ስእለት ለሕይወቴ አምላክ ነው።**

**42:5-8** *መዝሙረኛው ራሱን መልሶ ማረጋገጥ ይሞክራል*። ይህም በሁለት ጥያቄዎች ቀርቧል፣ ቁጥር 5 ላይ። እሱም ለጥያቄዎቹ ምላሽ ሰጥቷል፡

1. "ተስፋ" ("መጠበቅ፣" ቢዲቢ 403፣ ኬቢ 407፣ *ሂፊልተተኳሪ*) በእግዚአብሔር
2. "እንደገናም አመሰግነዋለሁ – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል ተተኳሪ*) ስለ መገኘቱ ርዳታ"
3. "አስታውሳለሁ (ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ) አንተን"
   ሀ. ከዮርዳኖስ ምድር
   ለ. ከአርሞንኤም ተራራ (ቢዲቢ 356፣ ስሙ ብኪ ላይ እዚህጋ ብቻ ነው የብዙ የሚሆነው፣ ብሎም፣ "ከፍታዎች")
   ሐ. ሚዛር ተራራ ("ትንሹ ኮረብታ፣" ቢዲቢ 859፣ LXX) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ። እሱም የሚያመለክተው
      (1) ከአርሞንኤም ተራራ አጠገብ ያለ አነስተኛ ኮረብታ
      (2) የሞሪያ ተራራን የመጥቀሻ መንገድ፣ የኢየሩሳሌም መቅደስ ስፍራ

የዕብራይስጥ ቅኔ የሚያምታታ ዓይነት ነው! ምናባዊነቱም ዘወትር አሻሚ ነው (ዕዝል ተመልከት፡ የዕብራይስጥ ቅኔ፣ ገጽ xxi ላይ)።

**42:7** ምስያው ብርቱ ነው። "ቀላይ ቀላይን ትጠራለች" የሚነካ ነው፣ ግን አሻሚ። ስለምን ፏፏቴ ነው እየተናገረ ያለው?

1. የመዝሙረኛው እንባ፣ 42:3
2. የዮርዳኖስ ወንዝ ሸለቆ፣ እና የተራራ መነሻው፣ 42:6

ቀጣዩ ስንኝ እንደሚያመለክተው የችግር ዘይቤ ይሆናል፣ መዝሙረኛው የገጠመው (መዝ. 69:1-2፤ 88:7)። የያህዌ መሆናቸውን ተገንዘብ

1. የውኃ ፏፏቴዎች
2. ማዕበል
3. ሞገድ

እነርሱም መዝሙረኛውን የከበቡት (ቢዲቢ 716፣ ኬቢ 778፣ *ቃል* የተጠናቀቀ)! ታማኝ ተከታዮች በወደቀው ዓለም ይኖራሉ፣ ነገር ግን ያህዌ፣ "የሕይወቴ አምላክ ነው" ብለው ያምናሉ/ይታመናሉ (42:9ሐ)። "ለምንታው" (ለምን) አይታወቅም፣ ነገር ግን "ማን" የሚለው ከእኛ ጋር ነው፣ ይኸም ርግጠኛ ነው!

"የውኃ" ምስያ፣ በዚህ መዝሙር ላይ ባለ ብዙ እጥፋት (ገጽታ) ነው።

1. ወራጅ ውኃ፣ ቁ. 1 (ማለትም፣ ድርቅ)
2. ዕንባ፣ ቁ. 3 (ማለትም፣ ሕመም)
3. ወንዝ (ማለትም፣ ዮርዳኖስ)፣ ቁ. 6
4. ቀላይ፣ ቁ. 7
   ሀ. ስሜቶች
   ለ. እግዚአብሔር ሁከቱን ለማሸነፉ ምስያ፣ ዘፍጥረት 1 ላይ
5. የውኃ ፏፏቴ (ማለትም፣ የመደበቂያ ስፍራ በሰሜን፣ ምናልባትም ከውኃ ፏፏቴ ሥር)
6. ማዕበል/ሞገድ (ማለትም የችግር ጎርፍ)

**42፡8** የመዝሙረኛው ዕንባ ቀንና ሌት እንደ ምግቡ እንደሆነ (ቁ. 3)፣ አሁንም የያህዌ (ይህ ብቸኛው የያህዌ አጠቃቀም እንደሆነ ተገንዘብ መዝሙር ላይ፤ መጽሐፍ 2 የመዝሙር፣ ለመለኮት ኤሎሂምን በብዛት ይጠቀማል፣ መጽሐፍ 1 ያህዌን እንደሚጠቀም) ቸርነት እና ዝማሬ ባልንጀሮቹ ናቸው።

◘ **"ዝማሬው"** ይህ የያህዌ ቸርነት ውጤት ነውን (ሄስድ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7 ላይ) ወይስ ወይስ የእሱ ትይዩ? የያህዌ ዝማሬ ምንድነው? የመዝሙረኛው ጸሎት፣ ስንኝ 3 ላይ ያለው ከ "መዝሙሩ" ጋር እንዴት ይዛመዳል? እሱ ምናልባት የሚያመለክተው ከመዝሙረኛው ምስጋና ይዘት ጋር ነው፣ ለያህዌ ምሕረትና ታማኝነት። ዝርዝሩ ቅኔ አሻሚ ነው። ክብደቱን መፍቀድ አለብን እናም አንጓውም እንዲሰማን፣ እንዲሁም የስንኞቹ ትይዩነት ወደ አጠቃላዩ ምልከታ ይመሩናል! ዝርዝሮቹን አትግፉ! ዶክትሪናችሁን በተገለሉ የቅኔ ስንኞች ላይ አትገንቡ!

◘ **"የሕይወቴ አምላክ"** ታማኝ ተከታዮች ብቻቸውን አይደሉም፤ በሕይወታቸው ዓላማ አለ፤ ምሕረትን የተሞላ ፈጣሪ አለ፣ ከእነርሱ ጋር ለእነርሱ የሆነ! ምንም ነገር "እንዲያው አይሆንም" በታማኝ ተከታዮች ላይ (መዝሙር 139)።

**መዝሙር ፡ 42፡9-11**

**[9]እግዚአብሔርን፦ አንተ መጠጊያዬ ነህ ለምን ረሳኸኝ?**
**ጠላቶቼ ሲያስጨንቁኝ ለምን አዝኜ እመላለሳለሁ? እለዋለሁ።**
**[10]ጠላቶቼ ሁልጊዜ። አምላክህ ወዴት ነው? ባሉኝ ጊዜ**
**አጥንቶቼን እየቀለጣጠሙ ሰደቡኝ።**
**[11]ነፍሴ ሆይ፥ ለምን ታዝኛለሽ?**
**ለምንስ ታውኪኛለሽ?**
**የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ**
**በእግዚአብሔር ታመኚ።**

**42፡9-11** ሆን ተብለው የተቀመጡትን ትይዩዎች ትመለከታለህን፣ ቁጥር 3 እና 10፤ 5 እና 11 ላይ ያሉትን?

ይህ ማጠቃለያውን ዳግም እንደ ማጠናከር ነው። መዝሙረኛው ብቻውን እንዳለ ይሰማዋል (ቁ. 9ሀ)፣ እንደተጠቃ (ቁ. 9ለ)፣ እንደተዳከመ (ቁ. 11ሀ፣ለ)። እንዴት አድርጎ ነው ምላሽ የሚሰጠው?

1. መጠበቅ – የቁ. 5 ተመሳሳይ
2. ማመስገን – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊልተኳዳኝ*
3. የቁጥር 8ን አምላክ አስታወሰ፣ እንዲሁም የቀድሞውን የአምልኮ ጊዜ፣ ከእርሱ ጋር ቁጥር 4 ላይ። እምነት ወደፊት ያመላክታል፣ እንዲሁም በአለፉት የመታመን ድርጊቶች ላይ ይመሠረታል።

**42፡9 "ዐለቴ"** መዝሙር 18፡2 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

**42፡10** የጠላቶቼ ቃላት እጅግ ቆጥቋጭ መሆናቸውን መዝሙረኛው ይገልጻል፣ "አጥንቶቼን እየቀለጣጠሙ" በማለት። ቃላት ይጎዳሉ። ሊያጠፉም ይችላሉ። እነርሱም ልብን ይገልጻሉ፣ አንድ ቀንም እያንዳንዱ ሰው ለእግዚአብሔር ምላሽ ይሰጣል፣ ስለ ተናገረው/ተናገረችው ቃል (ማቴ. 12፡36-37)።

**42፡11መ** ይህ የመጨረሻ የስም ሐረግ የሚሠራው ቁጥር 8ሐ ላይ እንዳለው የስም ሐረግ ነው። እሱም ለእግዚአብሔር መገኘትና ክብካቤ አጽንዖት ይሰጣል! እሱ ከእኛ ጋር ለእኛ ነው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መጽሐፍ 2 ላይ (መዝሙር 42-72) መዝሙር ላይ ሁለት የመለኮት ስሞች አሉ፣ አዘውትረው የሚከሰቱ።

ሀ. ኤሎሂም
ለ. ያህዌ
ምን ማለት እንደሆኑ አብራራ።

2. “ሕያው አምላክ” የያህዌ ቅይይር እንዴት ይሆናል?
3. ደራሲው
   ሀ. ሌዋዊ?
   ለ. በስደት ነውን?
4. ሚዛር ተራራ የት ነው?
5. ማን ነው “አምላክህ ወዴት ነው” የሚለው?
6. መዝሙር 42 እና 43 በአንድ ወቅት አንድ መዝሙር ነበሩ ተብሎ የሚታሰበው ለምንድነው?

# መዝሙር 43
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጸሎት ለመታደግ<br>ኤምቲ መግ. የለውም<br>የመዝሙር 42 ቀጣይ | በችግር ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት | ጸሎት ለፈውስ ለምናኔ በመዘጋጀት ጊዜ | የአንዱ ጸሎት በስደት ጊዜ | የሌዋዊ ሰቆቃ በስደት |
| 43:1-2 | 43:1-2 | 43:1-2 | 43:1-2 | 43:1 |
| | | | | 43:2 |
| 43:3-4 | 43:3-4 | 43:3-4 | 43:3-4 | 43:3 |
| | | | | 43:4 |
| 43:5 | 43:5 | 43:5 | 43:5 | 43:5 |

## የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 43፡1-2**

**[1]አቤቱ፥ ፍረድልኝ፥ ከጽድቅ ከራቁ ሕዝብም ክርክሬን ተከራከር**
**ከሽንጋይና ከግፈኛ ሰው አድነኝ።**
**[2]አንተ አምላኬ ኃይሌም፥ ለምን ትተውኸኛለህ?**
**ጠላቶቼ ሲያስጨንቁኝ ለምን አዝኜ እመላለሳለሁ?**

**43፡1** ምክንያቱም

1. 42፡5 እና 11 ላይ ባለው አዝማች (ደጊመ-ቃል)፣ እሱም 43፡5 ላይ ዳግም የሚከሰተው
2. ኤምቲ ላይ መግቢያ ስለሌለው፣ መዝሙር 43 ላይ (መጽሐፍ 2 ላይ ብቸኛው መግቢያ የሌለው መዝሙር)

ይህ ምናልባት በአንድ ወቅት የመዝሙር 42 ክፍል ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ባልታወቀ ምክንያት የተከፋፈለ። የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ የኅዳግ ማስታወሻ (ገጽ 1330) የሚለው መዝሙር 42 ባለፈው ጊዜ ላይ የሚያተኩርበት ሐቅ፣ እንዲሁም መዝሙር 43 በመጻኢው ላይ፣ ለምንና የት እንደተከፋፈሉ ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል!

◘ **"ፍረድልኝ"** ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ 1047፣ ኬቢ 1622፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 7፡8፤ 26፡1፤ 35፡24) መሠረታዊ ፍችው "መፍረድ" ነው። መዝሙረኛው የፍርድ ቤት ቋንቋን ተጠቅሟል (መዝ. 17፡1-3)። ያህዌ ጻድቅና ፍትሐዊ ዳኛ ነው፣ በሰዎች *ሥራ* ሁሉ ላይ (መዝ. 9፡4)።

◘ **"ክርክሬን ተከራከር"** ይህም ደግሞ የፍርድ ቤት ዘይቤ ነው (ቢዲቢ 936፣ ኬቢ 1224፣ *ቃል ተተኳሪ*)። ያህዌ ብቸኛው ፍትሐዊና የማያዳላ ዳኛ ነው! ይኸው ተመሳሳይ ብርቱ ምናባዊ ምስያ ሮሜ 8፡31-39 ላይም አለ!

◘ **"ክፉ ሕዝቦች"** መዝምር 42 እና 43 በመነሻቸው አንድ መዝሙር መሆናቸው እውነት ከሆነ፣ እንግዲያውስ 42፡6 የሚለው ደራሲው በግዞት እንደሆነ ነው፣ ከዚያም "ክፉ ሕዝቦች" ሶርያን የሚያመለክቱ ሊሆኑ ይችላሉ።

አስገራሚ የሚሆነው ቀጣዩ ስንኝ ገላጭ ሐረግ መጠቀሙ ነው፣ "ሽንጋይና ከግፈኛ ሰው!" አንዱ የብዙ ቁጥር እና ጣዖት አምልኮ ወይም ወረራ ላይ ያተኮረ ገለጻን ሊጠብቅ ይችላል።

**43፡2** ሕይወት ከባድ፣ ፍትሕ-አልባ፣ እና ችግሮች ሳይታሰቡ የሚመጡበት ነው። ለምን እንደሆነ ሁላችንንም ይደንቀናል።

1. እግዚአብሔርን አስቀይሜው ይሆን
2. የእግዚአብሔርን ሕግ ጥሼ ይሆን
3. ይህ የኃጢአት ፍርድ ይሆን፣ ወይስ በነሲብ የሚደርስ ከፉ ሁኔትና ሰዎች በወደቀው ዓለም ላይ ይሆን?

*መዝሙረኛው "ለምን" ብሎ ይጠይቃል (ቁ. 2)፣ እንዲሁም ሰዎች ሁሉ!*

ይህ የብኪ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ እንደሆነ አስታውስ፣ ዘውጉም በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) በደንብ የሚታወቅ። እሱም ጥያቄዎችን ያነሣል፣ ሰዎች ሁሉ የሚጠይቋቸውን። ለእስራኤል ጥያቄዎቹ የሚያያዙት ከያህዌ ጋር እና በሙሴ በኩል ከሰጠው መገለጡ ጋር ነው። ብኪ ጥያቄዎችን ሁሉ አይመልስም፣ አኪ በሚያደርግበት ተመሳሳይ መንገድ። ይህ ለውጥ ነው።

1. ቀጣይነት ያለው መገለጥ
2. አዲስ ኪዳን
3. የከፉው ምሥጢር

◘ **"የኃይሌ አምላክ"** ይህ ተደጋጋሚ አዝማች (ቃል) ነው (ቢዲቢ 731፣ ማለትም፣ የደኅንነት ወይም የመጠበቅ ስፍራ፣ ዘወትርም "መታመኛ" ተብሎ የሚተረጎም መዝ. 27:1፤ 28:7-8፤ 31:2፣4፤ 37:39፤ 52:7፤ ኢሳ. 17:10፤ 25:4፤ 27:5፤ ኤር. 16:19)። ታማኝ ተከታዮች ዘወትር ማወቅ ይችላሉ፣ ያህዌ የእነርሱ ተስፋ፣ መጠጊያ፣ እና የደኅንነት ስፍራ መሆኑን በችግሮች እና በግጭቶች መሐል፣ በዚህ በወደቀው ዓለም። ሆኖም፣ ይህ ሰላም በአግባቡ መያዝ ይኖርበታል። እሱም የእምነት ድርጊት እና ርዕዮተ-ዓለም ነው፣ ከአሁኑ እውነታ ተሸከርካሪ ሁኔታ ጋር የማይዛመድ!

◘ **"ጠላቶቼ ሲያስጨንቁኝ ለምን አዝኜ እመላለሳለሁ?"** ይህ ከመዝ. 42፡9 ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው።

***መዝሙር ፡ 43፡3-4***

***³ብርሃንህንና እውነትህን ላክ እነርሱ ይምሩኝ፥***
***ወደ ቅድስናህ ተራራና***
***ወደ ማደሪያህ ይውሰዱኝ።***
***⁴ወደ እግዚአብሔር መሠዊያ፥***
***ጒልማስነቴንም ደስ ወዳሰኘት***
***ወደ አምላኬ እገባለሁ አቤቱ አምላኬ፥ በበገና አመሰግንሃለሁ።***

**43፡3 "ላክ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 1018፣ ኬቢ 1511፣ *ቃል ተተኳሪ*) የጸሎት ጥያቄ ነው፣ ያህዌን ሰዋዊ የሚያደርግ

1. ብርሃን — ቢዲቢ 21
   ሀ. በያህዌ ሞገስ እንዳለው – መዝ. 4:6፤ 44:3
   ለ. እንደ መሪ – ሚኪያስ 7:8
   ሐ. እንደ ፍጻሜ ዘመን ብርሃን – ኢሳ. 9:2 (የኢየሱስ የመጀመሪያ ምፅአት)፤ ኢሳ. 60:19-20 (የኢየሱስ ዳግም ምጽአት)
2. እውነት – ቢዲቢ 54 (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 12:1 ላይ)
   ሀ. ለያህዌ ዘወትር የሚሰጠው ዘወትር የሚተረጎመው "ታማኝነት" ነው – መዝ. 40:10፤ 71:22፤ 115:1፤ 138:2
   ለ. ዘወትር ሰውኛ ይሆናል፣ እንደ ያህዌ ወኪሎችና መልእክተኞች – መዝ. 40:11፤ 43:3፤ 57:3፤ 85:10፤ 89:14

"ብርሃን" እና "እውነት" ምን እንደሚያደርጉ ተገንዘቡ።

1. ይምሩኝ – ቢዲቢ 634፣ ኬቢ 685፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ*
2. ወደ ቅዱሱ ተራራህ ይውሰዱኝ| – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*

◘ **"ቅዱስ ተራራ"** ይህ ከብዙዎቹ አንደኛው መንገድ ነው በኢየሩሳሌም በሞሪያ ተራራ ያለውን መቅደስ ለመጥቀስ። እሱም ዘወትር ይጠራል (ዘወትር "ቅዱስ" ከሚለው ቅጽል ጋር)፡

1. ጽዮን
2. ቤት
3. መቅደስ
4. ማደሪያ
5. ቤተ መቅደስ
6. ተራራ
7. የእግዚአብሔር ከተማ

እዚህ ትይዩ የሆነው ከ "ማደሪያ ስፍራዎችህ" ከሚለው ጋር ነው (መዝ. 46:4፤ 84:1)። የብዙ ቁጥሩ የሚገልጸው የመቅደሱን ዙሪያ ገባ ሕንጻዎች ባጠቃላይ ወይም የግርማውን ብዙኅነት ነው (NIDOTE፣ ቅጽ. 2፣ ገጽ. 1132)።

**43፡4** መዝሙረኛው መሄድን ይሻል (ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል ተጓዳኝ*) ወደ መቅደስ እና ምስጋና ማቅረብ (ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*) ለእግዚአብሔር በመሰንቆ (ቢዲቢ 490፣ ማለትም፣ የከር የሙዚቃ መሣርያ፣ መዝ. 33:2)።

**መዝሙር ፡ 43፡5**

[5]**ነፍሴ ሆይ፥ ለምን ታዝኛለሽ?**
**ለምንስ ታውኪኛለሽ?**
**የፊቴን መድኃኒት አምላኬን አመሰግነው ዘንድ**
**በእግዚአብሔር ታመኚ።**

**43፡5** ይህ የተደገመ አዝማች ነው ከመዝ. 42፡5፣11። ይህ ነው እነዚህን ሁለት መዝሙሮች አንድ የሚያደርጋቸው።

**የውይይት ጥያቄዎች** — መዝሙር 42 ላይ ያለውን ዝርዝር ተመልከት። እነዚህ ሁለት መዝሙሮች ከጽሑፍ አኳያ አንድ ምድብ ናቸው።

## መዝሙር 44
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የቀደመው መታደግ እና የአሁኑ ችግር<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ። የቆሬ ልጆች ትምህርት | የሚታወስ መታደግ በአሁኑ ውርደት | የመታደግ ጸሎት ከብሔራዊ ጠላቶች | ጸሎት ለጥበቃ | ብሔራዊ ሰቆቃ |
| 44:1-3 | 44:1-3 | 44:1-3 | 44:1-3 | 44:1-2ሀ |
| | | | | 44:2ለ-3 |
| 44:4-8 | 44:4-8 | 44:4-8 | 44:4-8 | 44:4-5 |
| | | | | 44:6-8 |
| 44:9-16 | 44:9-16 | 44:9-12 | 44:9-12 | 44:9-10 |
| | | | | 44:11-12 |
| | | 44:13-16 | 44:13-16 | 44:13-14 |
| | | | | 44:15-16 |
| 44:17-19 | 44:17-19 | 44:17-19 | 44:17-19 | 44:17-19 |
| 44:20-26 | 44:20-22 | 44:20-22 | 44:20-22 | 44:20-22 |
| | 44:23-26 | 44:23-26 | 44:23-24 | 44:23-24 |
| | | | 44:25-26 | 44:25-26 |

### **የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. የመከፈቻዎቹ አንጓዎች በሰው ልጅ ዕቅድና ጥረት ውድቀት እና በያህዌ የተሳካና ባለ-ዓላማ ዕቅድ መካከል ያለውን ተቃርኖ የሚያሳዩ ናቸው።

ለ. እግረ መንገዱን ይህ መዝሙር ተመሳሳይ የሚሆነው
1. ዘዳግም 32 ጋር
2. ነህምያ 9
3. መዝሙር 78

ታሪክነታቸውም ከእስራኤል ያልታመነ መሆንና ከያህዌ ታማኝነት አኳያ ነው፣ በድሮዎቹ ዓመታት (ዘጸአት፣ ምድረ-በዳ፣ ድል፣ መሳፍንት)።

ሐ. ይህ መዝሙር በግልጽ የተጻፈው እስራኤል በስደት ውስጥ ካለፈ በኋላ ነው። የእሱም ትኩረት ብሔራዊ እንጂ ግለሰባዊ አይደለም።

መ. እሱም ደግሞ ደጋግሞ የሚያስቀምጠው ያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዓላማ እንዳለው ነው። እባክዎትን የሚከተሉትን ልዩ ርዕሶች በቀጥታ የድረ-ገጽ መስመር ይመልከቱ (www.freebiblecommentary.org)።
1. የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ

2. የብኪ የኪዳን ተስፋዎች ከአኪ የኪዳን ተስፋዎች እጅግ የተለዩ የሚመስሉት ለምንድነው?

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 44፡1-3**

**[1]አቤቱ፥ በጆሮአችን ሰማን፥**
**አባቶቻችንም በዘመናቸው**
**በቀድሞ ዘመን**
**የሠራኸውን ሥራ ነገሩን።**
**[2]እጅህ አሕዛብን አጠፋች፥**
**እነርሱንም ተከልህ**
**አሕዛብን ሣቀይኻቸው**
**አሳደድኻቸውም።**
**[3]በሰይፋቸው ምድርን አልወረሱም**
**ክንዳቸውም አላዳናቸው**
**ቀኝህና ክንድህ የፊትህም ብርሃን ነው እንጂ**
**ወድደሃቸዋልና።**

**44፡1-3** ይህ አንጓ ዳግም ይዘረዝራል (የተጠናቀቁ ግሦች፣ ዘዳ. 32፡7) ያህዌ ለእስራኤል ያደረገውን ሁሉ፣ በኢያሱ ድል ወቅት። ድሉ የዘፍ. 15፡12-21 ተስፋ ፍጻሜ ሆነ። የዘፍጥረት ምንባብ ለያህዌ ሚና አጽንዖት እንደሚሰጥ ተገንዘቡ (ማለትም፣ ቅዱስ ጦርነት) በተስፋው። ያህዌ ይሠራ ነበር፣ አብርሃም ሲያንቀላፋ! ድሉ የያህዌ ድል ነው፣ የእስራኤል ወታደር ሳይሆን (ቁ. 3)።

**44፡1 "ሰማን"** የአይሁድ ዓመታዊ በዓላት ኢጋጣሚነታቸው አዲሱን ትውልድ ለማስተማር ነበር፣ ስለ እግዚአብሔር የማዳን ሥራዎች (ዘጸአት 12፤ ዘዳ. 6፡20-25፤ ተደጋጋሚውን ሐረግ ተገንዘብ፣ "ልጆቻችሁ በጠየቋችሁ ጊዜ..." ዘጸ. 12:26፣27፤ 13:14-15፤ ዘዳ. 6:20-35፤ ኢያ. 4:6-7፣21-24)። እሱም የእያንዳንዱ የአማኝ ትውልድ መንፈሳዊ ኃላፊነት ነው፣ አዲሱን ትውልድ ስለ እግዚአብሔር ማስተማር፣ ስለ ባሕርዩ፣ እና ስለ ማዳን ሥራው።

**44፡2 "አሕዛብ... ሕዝቦች"** ይህ የሚያመለክተው የከነአንን ነባር ነዋሪዎች ነገዶች ነው። ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

### ልዩ ርዕስ፡ ቅድመ-እስራኤላውያን የፍልስጥኤም ነዋሪዎች

ሀ. የበርካታ ሕዝቦች ዝርዝር አለ፡፡
1. ዘፍጥረት 15፡19-21 /10/
   - ሀ. ቄናውያን
   - ለ. ቀኔዛውያን
   - ሐ. ቀድሞናውያን
   - መ. ኬጢያውያን
   - ሠ. ፌርዛውያን
   - ረ. ራፋይም
   - ሰ. አሞራውያን
   - ሸ. ከነአናውያን
   - ቀ. ጌርጌሳውያን
   - በ. ኢያቡሳውያን
2. ዘጸአት 3፡17 /6/
   - ሀ. ከነአናውያን
   - ለ. ኬጢያውያን
   - ሐ. አሞራውያን
   - መ. ፌርዛውያን
   - ሠ. ኤውያውያን
   - ረ. ኢያቡሳውያን
3. ዘጸአት 23፡28 /3/
   - ሀ. ኤውያውያን
   - ለ. ከነአናውያን
   - ሐ. ኬጢያውያን
4. ዘዳግም 7፡1 /7/
   - ሀ. ኬጢያውያን
   - ለ. ጌርጌሳውያን
   - ሐ. አሞራውያን
   - መ. ከነአናውያን
   - ሠ. ፌርዛውያን
   - ረ. ኤውያውያን
   - ሰ. ኢያቡሳውያን
5. ኢያሱ 24፡11 (7)
   - ሀ. አሞራውያን
   - ለ. ፌርዛውያን
   - ሐ. ከነአናውያን
   - መ. ኬጢያውያን
   - ሠ. ጌርጌሳውያን
   - ረ. ኤውያውያን
   - ሰ. ኢያቡሳውያን

ለ. የስሞቹ መነሻ ርግጠኝነት የለውም፣ ከታሪካዊ መረጃ እጥረት የተነሣ። ዘፍጥረት 10፡15-19 በርካቶቹን ያካትታል፣ ከከነአን ጋር በተያያዘ፣ የካም ልጅ።

ሐ. አጭር መግለጫ ከዘፍ. 15፡19-21 ረጅም ዝርዝር

1. ቄናውያን — ቢዲቢ 884
   - እስራኤላውያን ያልሆኑ

- ከ“ብረት አቅላጭ” ወይም “ብረት አፍሳሽ” ጋር ይዛመዳል፣ እሱም የብረት ሥራን ወይም ሙዚቃን የሚያመለክት (ዘፍ. 4፡19-22)
- ከሲና በስተሰሜን ወደ ኬብሮን ሲል ካለው ስፍራ ጋር የሚያያዝ
- ከሙሴ አማት ስም ከዮቶር ጋር የሚያያዝ (መሳ. 1፡16፤ 4፡11)

2. ቄኔዛውያን — ቢ.ዲ.ቢ. 889
   - የአይሁድ ዘመዶች
   - የኤዶም ጎሳ (ዘፍ. 15፡19)
   - በኔጌቭ የኖሩ
   - ወደ ይሁዳ የተጠቃለሉ ሊሆኑ የሚችሉ (ዘኊ. 32፡12፤ ኢ.ያ. 14፡6፥14)
3. ካድሞናውያን — ቢ.ዲ.ቢ. 870 II
   - እስራኤላውያን ያልሆኑ፣ የእስማኤል ዝርዮች ሊሆኑ ይችላሉ (ዘፍ. 25፡15)
   - “ከምስራቃውያን” ጋር የሚዛመድ ስም
   - በኔጌቭ የሚኖሩ
   - “በምስራቅ የሚኖሩ ሰዎች” ጋር ሊዛመድ ይችላል (ኢዮብ 1፡3)
4. ኬጢያውያን — ቢ.ዲ.ቢ. 366
   - እስራኤላውያን ያልሆኑ
   - የሄዝ ዝርያ
   - ከአናቶሊያ መንግሥት (ትንሹ እስያ፣ ቱርክ)
   - እጅግ በቅርቡ በከነአን የነበሩ (ዘፍጥረት 23፤ ኢ.ያ. 11፡3)
5. ፌርዛውያን — ቢ.ዲ.ቢ. 827
   - እስራኤላውያን ያልሆኑ፣ ሁሪያውያን ሊሆኑ ይችላሉ
   - በይሁዳ ዱር ስፍራ ይኖሩ የነበሩ (ዘፍ. 34:30; መሳ. 1:4; 16:10)
6. ራፋም — ቢ.ዲ.ቢ. 952
   - እስራኤላውያን ያልሆኑ፣ ግዙፋን ሊሆኑ ይችላሉ (ዘፍ. 14:5; ዘኍ. 33:33; ዘዳ. 2:10-11,20)
   - ከዮርዳኖስ ምስራቃዊ ዳርቻ ይኖሩ የነበሩ (ዘፍ. 15:20; ኢ.ያ. 12:4; 13:12; ዘዳ. 2:8-11,20; 3:13) ወይም ምዕራባዊ ዳርቻ (ኢ.ያ. 15:8; 17:15; 2 ሳሙ. 5:18,22; 23:13; 1 ዜና. 20:4)
   - የተዋጊዎች/ጀግኖች ዘሮች
7. አሞራውያን — ቢ.ዲ.ቢ. 57
   - የሰሜናዊ ምዕራብ ሴማዊ ሕዝቦች ወገን፣ ከካም (ዘፍ. 10፡16)
   - ለከነአን ኗሪዎች አጠቃላይ (የወል) መጠሪያ የሆነ (ዘፍ. 15:16; ዘዳ. 1:7; ኢ.ያ. 10:5; 24:15; 2 ሳሙ. 21:2)
   - ስሙ “ምዕራብ” የሚል ሊሆን ይችላል
   - አይኤስቢኢ፣ ቅጽ 1 ገጽ 119፣ የሚለው ቃሉ የሚገልጸው
     ሀ. የፍልስጥኤምን ኗሪዎች ባጠቃላይ
     ለ. የተራራማውን ሀገር ሕዝብ፣ ከባሕሩ ዳር ያለውን ሜዳ አፍዛዣ
     ሐ. የተወሰኑ ሕዝብ ወገኖች፣ በገዛ ራሳቸው ንጉሥ
8. ከነአናውያን — ቢ.ዲ.ቢ. 489
   - ከካም (ዘፍ. 10፡15)
   - የከነአን ነገዶች ሁሉ አጠቃላይ (የወል) መጠሪያ፣ ከዮርዳኖስ በስተምዕራብ
   - የከነአን ፍች ርግጠኝነት የለውም፣ “ነጋዴ” ወይም “ቀይ-ሐምራዊ አቅላሚ” ሊሆን ይችላል
   - በባሕሩ ዳርቻ ሜዳ ላይ ይኖሩ የነበሩ የሕዝብ ወገኖች (ዘኍ. 13፡29)
9. ጌርጌሳውያን — ቢ.ዲ.ቢ. 173
   - ከካም (ዘፍ. 10፡16) ወይም ቢያንስ “ከከነአን ልጆች [ማለትም፣ አገር]” አይኤስቢኢ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 1232)
10. ኢያቡሳውያን — ቢ.ዲ.ቢ. 101
    - ከካም (ዘፍ. 10፡16)
    - ከኢያቡስ/ሳሌም/ኢየሩሳሌም ከተማ (ኢ.ያ. 15፡63፤ መሳ. 19፡10)
    - ሕዝ. 16፡3፣45 የሚያስረግጠው እነርሱ ድብልቅ ሕዝቦች እንደሆኑ ነው፣ ከአሞራውያንና ከኬጢያውያን
11. ኤውያውያን — ቢ.ዲ.ቢ. 395
    - ከካም (ዘፍ. 10፡17)
    - በLXX ኤዊያዊ (ሆራይቲ) በሚል ተተርጉሟል (ዘፍ. 34:2; 36:20-30; ኢ.ያ. 9:7)
    - ከዕብራይስጡ ቃል “ዋሻ” ሊሆን ይችላል፣ ስለዚህም የዋሻ ኗሪዎች

– እነርሱ በሊባኖስ ደጋማ ስፍራዎች ይኖሩ ነበር (ኢያ. 11፡3፤ መሳ. 3፡3)። 2 ሳሙ. 24፡7 ላይ እነርሱ ከጢሮስና ሲዶና ቀጥለው ተዘርዝረዋል

◘ **"ተከልሃቸው"** ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ይህ አሁንም የሚጠቅሰው የከነአንን ነገዶች ነው (LXX)። ብኪ ያህዌን የሚመለከተው እንደ ሁሉንም የሕዝብ ወገኖች እንዳቋቋመ ነው (ዘዳ. 32፡8)። ዘፍጥረት 15፡12-21 የሚያስረግጠው የከነአን ነዋሪዎች የተባረሩት በኃጢአታቸው እንደሆነ ነው፤ እስራኤልም ኃጢአት ስትሠራ እሷም ደግሞ ትባረራለች (መዝሙር 78)።

አእቅ፣ የተእቅ፣ እና አእት መጽሐፍ ቅዱስ የሚገምቱት ቁጥር 2 የሚዛመደው ከ

1. ከነአን ሕዝቦች፣ 44፡2ሀ፣ሐ
2. እስራኤላውያን በኢያሱ ሥር፣ 44፡2ለ፣መ (ዘጸ. 15፡17፤ ኤር. 45፡4)

**44፡3** የእስራኤል ወታደር አይደለም፣ የያህዌ ብርታት እንጂ የእርሱን ዓላማ የሚያቀዳጀው፣ እስራኤል ግብፅን እንዲለቅ ያስደረገው፣ ወደ ከነአንም እንዲጓዝ፣ የአገሬውንም ነገዶች እንዲወርስ!

በመካከል ያሉትን ትይዩዎች ተገንዘብ

1. ቀኝ እጅህ
2. ክንድህ
3. የመገኘትህ ብርሃን

ቁጥር 3 የሚጠቅሰው ሼከናህን ነው የክብር ደመና፣ በምድረ-በዳ መንከራተት ዘመን።

◘ **"ወድደሃቸዋልና"** ይህ ያህዌ ለአብርሃም የሰጠው ተስፋ ዓላማ ነው።

1. ዘር (ማለትም፣ ዝርያዎች)
2. ምድር
   ሀ. አብርሃም – ዘፍ. 12:7፤ 13:15፤ 15:18
   ለ. እስራኤል – ዘፍ. 26:3
   ሐ. ያዕቆብ – ዘፍ. 28:13

"ወድደሃቸዋልና" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 953፣ ኬቢ 1280፣ ቃል የተጠናቀቀ) የሚጠቅሰው የኪዳኑን ዓላማ ነው (ዘፍ. 12:3) ሰዎችን ሁሉ ወደ ራሱ ለማምጣት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመቤዠት ዕቅድ መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)። ያህዌ አብርሃምንና ዘሩን ለመጠቀም ፈለገ (ዘዳ. 4:37፤ 7:7-8፤ 10:15) የአዳም ወንዶችና ሴቶች ልጆች ሁሉጋ ለመድረስ።

**መዝሙር ፡ 44፡4-8**

**[4]አምላኬና ንጉሤ አንተ ነህ**
**ለያዕቆብ መድኃኒትንህ እዘዝ።**
**[5]በአንተ ጠላቶቻችንን እንወጋቸዋለን፥**
**በስምህም በላያችን የቆሙትን እናዋርዳቸዋለን።**
**[6]በቀስቴ የምታመን አይደለሁምና፥**
**ሰይፌም አያድነኝምና**
**[7]አንተ ግን ከጠላቶቻችን አዳንኸን፥**
**የሚጠሉንንም አሳፈርሃቸው።**
**[8]ሁልጊዜ በእግዚአብሔር እንከብራለን፥**
**ስምህንም ለዘላለም እናመሰግናለን። ሴላህ።**

**44፡4-8** የመጀመሪያው አንጓ በተጠናቀቁ ግሦች የተሞላ ሲሆን፣ ያለፈውን በሚገልጹ፣ ይኼኛው፣ ባልተጠናቀቁ የተሞላ ነው፣ የአሁኑን በሚጠቅሱ። ሁለቱም የሚገልጹት ስለ "ቅዱስ ጦርነት" ወይም "እግዚአብሔር እንደ ተዋጊ" የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ ነው። ያህዌ (ወይም ስሙ፣ ቁ. 5፣8) የእስራኤል ድል ምንጭ ነው፣ የእነርሱ ወታደር ሳይሆን።

**44፡4 "አንተ ንጉሤ ነህ"** ያህዌ እንደ ንጉሥ መቆጠሩ የመጣው ከ1 ሳሙ. 8፡7 ይሆናል። የእስራኤላውያን ንጉሥ የያህዌ አገዛዝ እና ንግሥና ምድራዊ ተወካይ ብቻ ነበር፣ (ኢሳ. 24:23፤ 52:7፤ 93:1፤ 96:10፤ 97:1፤ 99:1)። በአይሁድ ሥነ-ጽሑፍና የአምልኮ ሥርዓት፣ ያህዌ "የዩኒቨርስ ንጉሥ" ተብሎ ይጠራል።

◘ **"ለያዕቆብ ድልን እዘዝ"** ይህ የጥያቄ ተተኳሪ ነው (ቢዲቢ 845፣ ኬቢ 1010፣ ፔይል ተተኳሪ።)

"ድል" የሚለው ቃል በጥሬው "መድኃኒት" ነው (ቢዲቢ 447)። በብኪ እሱ የሚጠቅሰው ከሥጋዊ ችግሮችና ከጠላት መዳን ነው።

ማለት የሚቻለውም የኤሎሂም የመጨረሻው ፊደል፣ ከቀጣዩ ቃል ጋር ሊሄድ እንደሚችል ነው፣ "አዛዡ" የሚል ቃል በመፍጠር (ኤቢ፣ ገጽ 265)፣ እሱም "ንጉሤ" ከሚለው ጋር ትይዩ የሚሆን። ኤቢ ቀጣዩም ሐረግ ትይዩ መጠሪያ እንደሆነ ይገልጻል፣ "የያዕቆብ መድኃኒት።"

◘ **"ለያዕቆብ"** ይህ ያህዌ ለአባቶች የሰጠው ተስፋ ጠቃሽ ነው (ማለትም፣ አብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ፣ ዘፍጥረት 12-35)። ያህዌ ግልጽ የሆነ ዘላለማዊ የመዋጀት ዓላማ አለው፣ ለዓለም ሁሉ፣ እስራኤልና ኢየሱስ ቁልፍ ይዘቶች የሆኑበት (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)!

**44፡8** የቁጥር 8ን ትይዩነት ተገንዘብ።

1. *መመካት — ምስጋና ማቅረብ*
2. *ቀኑን ሁሉ — ዘላለም*

◘ **"ሴላህ"** *መግቢያ ለመዝሙር ተመልከት፣* VII *እና መዝ.* 3፡2 *ማስታወሻ ላይ።*

***መዝሙር ፡ 44፡9-16***

**[9]አሁን ግን ጠላኸን አሳፈርኸንም፥**
**ከሠራዊታችንም ጋር አትወጣም።**
**[10]ከጠላቶቻችንም ፊት ወደ ኋላችን መለስኸን፥**
**የሚጠሉንም ተነጣጠቁን።**
**[11]እንደ በጎች ሊበሉን ሰጠኸን፥**
**ወደ አሕዛብም በተንኸን።**
**[12]ሕዝብህን ያለ ዋጋ ሰጠህ፥**
**በመለወጣቸውም ትርፍ የለም።**
**[13]ለጎረቤቶቻችን ስድብ፥**
**በዙሪያችንም ላሉ መሣቂያና መዘበቻ አደረግኸን።**
**[14]በአሕዛብ ዘንድ ምሳሌ፥**
**በሕዝብም ዘንድ የራስ መንቀሳቀሻ አደረግኸን።**
**[15]ጕስቍልናዬ ሁልጊዜም በፊቴ ነው፥**
**የፊቴም እፍረት ሸፈነኝ።**
**[16]ከሚሳደብና ከሚላገድ ቃል የተነሣ፥**
**ከጠላትና ከቂመኛ ፊት የተነሣ ነው።**

**44፡9-16** ይህ አንጻ ግልጽ የሆነ ጽንፍ የተገላቢጦሽ ነው የ44፡1-3 እና 4-8። ያህዌ ለእስራኤል ከመዋጋቱ ይልቅ (ማለትም፣ 44፡9ለ፤ መዝ. 60፡10፤ 108፡11)፣ እንርሱኑ ተዋጋ። ለምን እንደሆነ ግልጽ አድርጎ አላስቀመጠም፣ ነገር ግን ችግሩ ኪዳንን አለመታዘዝ እና የሴው መዘዝ ነበር (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)።

አስፈሪው ውጤት ወታደራዊ ሽንፈት አልነበረም፣ ግን ስደት፣ ባርነት፣ ውርደት እንጂ!

**44፡9 "አሁን ግን ጠላኸን"** ይህ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ 276፣ ኬቢ 276፣ ቃል የተጠናቀቀ) ዘወትር በመዝሙር ጥቅም ላይ ይውላል፣ ያህዌ የኪዳኑን ሕዝቦች ሲጠላ (መዝ. 44፡9፣23፤ 60፡1፣10፤ 74፡1፤ 77፡7፤ 108፡11)። ምክንያቱ ለምን እንደሆነ ትልቁ ጥያቄ ነው።

1. ኪዳንን አለመታዘዝ (ማለትም፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)
2. ከያህዌ ጋር ያላቸው ግንኙነት (ማለትም፣ ኢዮብ፣ መዝሙር 73፣ ዕንባቆም)
3. የታማኝነታቸው መፈተን ከበረከት ጋር አይዛመድም (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይፈትናል፣ መዝ. 11፡4ለ-5)

መዝሙሩ ይሄንን አይመልስም፣ ከ44፡22 የሙሉው መዝሙር ቁልፍ ከመሆኑ በቀር።

***መዝሙር ፡ 44፡17-19***

**[17]ይህ ሁሉ በእኛ ላይ ደረሰ፥ አልረሳንህም፥**
**ኪዳንህንም አልወነጀልንም።**
**[18]ልባችን ወደ ኋላው አልተመለሰም፥**
**ፍለጋችንም ከመንገድህ ፈቀቅ አላለም**
**[19]በክፉ ስፍራ አዋርደኸናልና፥**
**በሞት ጥላም ሰውረኸናልና።**

**44፡17-19** ይህ አንጻ ኃላፊነትን ለመቀበል መሞከር ነው። እስራኤል ንጽሕናውን ያስረግጣል።

1. አልረሳንህም
2. ኪዳንህንም አልወነጀልንም
3. ልባችን (የወል) ወደ ኋላው አልተመለሰም
4. ፍለጋችንም ከመንገድህ ፈቀቅ አላለም

ይህ የንጽሕና ማስረገጥ በተከታዩም አንጻ ይቀጥላል (ዝከ.ቁ.20-22)። ይህ ለአንዳንድ እስራኤላውያን እውነት ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ለብዙዎቹ አይሆንም፣ ለአብዛኛው ታሪካቸው (ዘዳግም 32፤ መዝሙር 78፤ ነህምያ 9)።

ቁጥር 19 ከሥነ-መለኮት አኳያ ከኢዮብ ጋር ይመሳሰላል፣ እዚያም እሱ እግዚአብሔር የእርሱን ጉዳይ በክፉ እንዳየበት። መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይከሳል፣ በእነርሱ ላይ ተቃውሞ በማድረጉ፣ ተገቢ ባልሆነ ሁኔታ!

ለተለየ ትርጉም ዴሪክ ኪድነር፣ ቲንዳሌ የብኪ ሐተታ (ኮሜንተሪ)፣ ቅጽ15፣ ገጽ 185-186 ተመልከት።

**44፡17 "ኪዳንህን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 25፡10 ላይ።

**44፡19**
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

**አየተመት፣ አኢመቅ "አውሬ"**
**ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ "የባሕር አውሬ"**

በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለ ልዩነት አንድ ተናባቢ ነው።

1. አውሬ – ቢዲቢ 1072፣ תנים
2. የባሕር አውሬ – ቢዲቢ ןנּת

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 237) ለ "አውሬ" "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ)። ጀፒኤስአኤ ለሕዝ. 29:3፤ 32:2፣ እንደ ትይዩ ምንባብ ይሰጠዋል፣ ለ*tannin* (ማለትም፣ "የባሕር አውሬ፣" ዘፍ. 1:21፤ ኢዮብ 7:12)።

ከከነአናውን ሥነ-ጽሑፍ አኳያ የበረሀ ፍጥረታት ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውሉት በዘይቤአዊ ቋንቋ ለአሕዛብ ኃኔን ነው (ኢሳ. 13:21-22፤ 34:11-15፤ ኤር. 9:11፤ ሚክ. 1:8፤ ሰፉ. 2:4)።

◘ **"የሞት ጥላ"** መዝ. 23:4 ላይ ማስታወሻ ተመልከት። ያህዌ የኪዳን ሕዝቡን ለኢጋንንታዊ ኃይላት ትቷቸዋል፣ ለጣዖት አምላኪ ሃይማኖቶች እና ለሞት ግዛት!

## መዝሙር ፡ 44:20-26

**[20]የአምላካችንን ስም ረስተንስ ቢሆን፥**
**እጃችንንም ወደ ሌላ አምላክ አንሥተንስ ቢሆን፥**
**[21]እግዚአብሔር ይህንን አይመረምርም ነበርን?**
**እርሱ ልብ የሰወረውን ያውቃልና።**
**[22]ስለ አንተ ሁልጊዜም ተገድለናል፥**
**እንደሚታረዱም በጎች ሆነናል።**
**[23]አቤቱ፥ ንቃ ለምንስ ትተኛለህ?**
**ተነሥ፥ ለዘወትርም አትጣለን።**
**[24]ለምንስ ፊትህን ትሰውራለህ?**
**መከራችንንና ችግራችንንስ ለምን ትረሳለህ?**
**[25]ነፍሳችን በመሬት ላይ ተጐሳቍላለችና፥**
**ሆዳችንም ወደ ምድር ተጣብቃለችና።**
**[26]አቤቱ፥ ተነሥና እርዳን፥**
**ስለ ስምህም ተቤዠን።**

**44:20** ይህ የተለየ ጣዖት አምላኪነትን መካድ ነው። እነርሱ የሚያስረግጡት፣ ጣዖት አምላኪ ቢሆኑ ያህዌ ያውቀው ነበር (ቁ. 21፣ cf. መዝ. 7:9፤ 17:3፤ 26:2፤ 66:10፤ 139:23፤ ኤር. 11:20፤ 17:10፤ 20:12)።

◘ **"እጃችንን ማንሣት"** ይህ በጥሬው "ወደ ፊት መዘርጋት" ነው (ቢዲቢ 831፣ ኬቢ 975፣ ቃል ያልተጠናቀቀ)። ይህ አካላዊ የስግደት እንቅስቃሴ ነው፣ ዘወትርም ጸሎትን ያመለክታል (ዘጸ. 9:29፤ 2 ዜና. 6:12፤ እዝራ 9:5፤ ኢዮብ 11:13፤ መዝ. 28:2፤ 48:31፤ 88:9፤ 134:2፤ 141:2፤ 143:6)፣ ግን ደግሞ መሥዋዕትንም ያካትታል (ማለትም፣ ማንሣት) አንድ ዓይነት መሥዋዕት (እንስሳ፣ ዕጣን፣ እህል፣ ወይም ወይን)።

**44:2** ይህ መጠየቂያ ነው፣ እንደ ቁ. 19፣ ያህዌ እስራኤልን ለተወበት (ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ 409)። ጳውሎስ ይሄንን ቁጥር ተጠቅሟል ሮሜ. 8:36 ላይ፣ እናም የእግዚአብሔር ሰዎች ችግር ሊገጥማቸው እንደሚችል የሚያመለክት ይመስላል፣ በወደቀው ዓለም፣ ነገር ግን እርሱ ከእነርሱ ጋር ለእነርሱም ነው። ማንም በክርስቶስ ካለን ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለየን አይችልም (ሮሜ. 8:38-39)።

◘ **"ስለ አንተ"** አንዳንዶች ይሄንን ሐረግ የሚመለከቱት እንደ መዝሙሩ ቁልፍ ሥነ-መለኮታዊ ነጥብ አድርገው ነው። የእግዚአብሔር ሕዝቦች ይሳደዳሉ፣ በኃጢአታቸው ምክንያት ግን አይደለም፣ ነገር ግን ከእርሱ ጋር ባላቸው ግንኙነት እንጂ። ይህ ሐሳብ በግልጽ ይታያል፣ በኢየሱስ ሕይወት ላይ።

እኔ ርግጠኛ አይደለሁም በቂ ጽሑፋዊ ማስረጃ በዚህ መዝሙር ላይ ለመኖሩ፣ ይሄንን ሐሳብ ለማቅረብ!

**44:23-26** ይህ እንደ ተለየ አንጓ ነው የሚወሰደው አኪጀት፣ አየተመት ላይ። ተለጣጣቂ የጸሎት ጥያቄዎች አሉ (ተተኳሪ እና ተጽዕኗዊ)።

1. ራስህ ተነሥ፣ቁ. 23 – ቢዲቢ 734፣ ኬቢ 802፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 7:6፤ 35:23
2. ንቃ – ቢዲቢ 884፣ ኬቢ 1098፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 35:23
3. ለዘላለም አትጣለን – ቢዲቢ 276፣ ኬቢ 276፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 77:7
4. ተነሥ – ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 3:7፤ 7:6፤ 9:19፤ 10:12፤ 17:13፤ 74:22፤ 82:8፤ 132:8
5. ተቤዠን – ቢዲቢ 804፣ ኬቢ 911፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 25:22፤ 130:8 (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 19:14 ላይ)

**44:23 "ስለምንስ ትተኛለህ፣ ጌታ ሆይ?"** ይህ ሰውኛ ፈሊጣዊ ዘይቤ ነው (መዝ. 78:65)። ያህዌ (እዚህጋ አዶንያ ተብሎ ተጠርቷል) አይተኛም (መዝ. 121:4)፣ ነገር ግን ከእስራኤል ኃጢአት የተነሣ፣ ከእነርሱ ጋር ያለውን ኅብረት ያቋረጠ ይመስላል (ዝኪ. ቁ. 24-25)።

ለተሻለ አጭር ማብራሪያ የመጽሐፍ ቅዱስ ጠጣር አባባሎች፣ "አምላክ ይተኛልን?" የሚለውን ተመልከት (ገጽ 268-269)።

**44:24 "ለዘላለም አትተወን"** "ዘላለም" ሌላው ፈሊጥ ነው፣ ኅብረትን የሚያመለክት (መዝ. 103:9)። ዘላለም መስሏቸዋል። ነገር ግን እሱ ለጊዜው የሆነ የኅብረት መቋረጥ ነው፣ ንስሐን ለማነሣሣትና የረጅም ጊዜ ኅብረትን ለመመለስ።

**44፡25** ይህ ምናባዊ ነው፣ ለሰዎች አጸላለይ፣ አንድም በጉልበታቸው ተንበርከው ወይም መሬት ላይ ተዘርግተው። ይህ ያልተለመደ የአጸላለይ ሁኔታ ነው፣ እሱም ዘወትር ቆመው እጅ በመዘርጋትና ዓይንን ከፍቶ፣ ወደ ላይ በመመልከት ነበር። ሰሎሞን በጉልበቱ ተንበርኮ ጸልዮአል (2 ዜና. 6፡13)፤ ዳንኤል በጉልበቱ ተንበርኮ ጸልዮአል (ዳን. 6፡10)፤ ኢየሱስ በፊቱ ተደፍቶ ጸልዮአል፣ በጌቴሴማኒ (ማቴ. 26፡39)! እሱም ጽኑነትን ማሳያ መንገድ ነው!

**44:26 "ስለ ቸርነትህ"** ያህዌ የሚሠራው

1. ለአባቶቻቸው ስላለው ፍቅር (ማለትም፣ አባቶች)
2. ለአባቶቻቸው ስላለው ተስፋ
3. ለአብርሃም ኪዳን ባለው ሰፊ ዓላማ (ዘፍ. 12፡3፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)
4. ስለ ኪዳን ታማኝነቱ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7 ላይ) ለቃሉ (መዝ. 6:4፤ 109:21፣26፤ 119:149)

ስለ እስራኤል መልካምነት አይደለም (ዘዳ. 9:4-6፤ ሕዝ. 36:22-38)።

## ልዩ ርዕስ፡ የያህዌ የጸጋ ድርጊቶች ለእስራኤል

በግልጽ መቀመጥ የሚኖርበት ዘጸአት፣ የምድረ-በዳ እንክርት፣ እና ድል የያህዌ የጸጋ ድርጊቶች መሆናቸውን ነው፣ እስራኤል በድርጊቱ በሥራው ያገኛቸው ዋጋዎች ሳይሆኑ፡

1. እሱ ያህዌ "ለአባቶች" ባለው ፍቅር ነው – ዘዳ. 4:37-38፤ 7:8፤ 10:15
2. እስራኤል በቁጥር በመበርታቱ የሆነ አይደለም – ዘዳ. 7:7
3. በእስራኤል ብርታትና ኃይል አይደለም – ዘዳ. 8:17
4. በእስራኤል ጽድቅ ወይም መልካምነት አይደለም – ዘዳ. 9:5-6
5. ያህዌ እስራኤልን መውደዱን ቀጥሏል፣ በፍርድ መካከል እንኳ ቢሆን – ኤር. 31:3

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በዚህ መዝሙር ላይ የትኛው ዓይነት የኪዳን ገጽታ ነው ጥያቄ ያስነሣው?
2. ይህ መዝሙር ስለ እስራኤል ፖለቲካዊ መዋቅር ምን ያስተምራል?
3. እስራኤል ለምን ተሸነፈ?
4. አምላክ ምላሽ እንዲሰጥ ለምን ተጠየቀ?

# መዝሙር 45
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእት** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| *የንጉሥ ጋብቻ ማክበሪያ መዝሙር*<br>*<u>ኤምቲ መግቢያ</u>*<br>*ለመዘምራን አለቃ፤ እንደ ሾሻኒም፣ የቆሬ ልጆች ትምህርት። የፍቅር መዝሙር፡* | *የመሢሑ እና የሙሽራው ክብር* | *የንጉሣዊ ጋብቻ መወድስ* | *የንጉሣዊ ጋብቻ መዝሙር* | *ንጉሣዊ ጋብቻ* |
| 45:1-2 | | | | |
| | 45:1-5 | 45:1 | 45:1 | 45:1 |
| | | 45:2-3 | 45:2-3 | 45:2 |
| 45:3-5 | | | | |
| | | | | 45:3ሀ-4ሀ |
| | | 45:4-5 | 45:4-5 | 45:4ለ-5 |
| 45:6-9 | | | | |
| | 45:6-9 | 45:6-9 | 45:6-9 | 45:6-7a |
| | | | | 45:7b-8ሀ |
| | | | | 45:8ለ-9 |
| 45:10-12 | | | | |
| | 45:10-12 | 45:10-13ሀ | 45:10-12 | 45:10-13ሀ |
| 45:13-15 | | | | |
| | 45:13-17 | 45:13ለ-15 | 45:13-15 | 45:13ለ-16 |
| 45:16-17 | | | | |
| | | 45:16-17 | 45:16-17 | |
| | | | | 45:17 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ሦስተኛው አንቀጽ*
4. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙሩ አንድ የእስራኤል ንጉሥን ያወድሳል።
1. ሰሎሞን ሊሆን ይችላል፣ በጋብቻዎቹ ጊዜ /አአመመቅ ኅዳግ/
2. አካብ እና ከኤልዛቤል ጋር ጋብቻው /የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 1332/
3. ዳዊት /ኢብን ዕዝራ/
4. መሢሕ /የኢብን ዕዝራ ሁለተኛ አማራጭ እና የቤተ ክርስቲያን አባቶች/

ለ. መዝሙሩ በአንዳንዶች የሚታየው መሢሐዊ እንደሆነ ነው /የተውላጠ ስሞቹን በትልልቅ ፊደላት መጻፍ ተገንዘብ/ ነገር ግን በዐቢይ ምድባዊ መልኩ። ከታሪካዊነት አኳያ እሱ የሚገጥመው
1. ግነታዊ ንጉሣዊ ቋንቋ፣ የጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/
2. የሰሎሞን ጋብቻ እሱ የሚገዛቸው ሰፊ ግዛት /ኢምፓየር/ የሕዝብ ወገኖች የተገኙበት

ሐ. ሁሉም የእስራኤል ነገሥታት የሚወሰዱት ያህዌን እንደሚወክሉ ተደርገው ነው /1 ሳሙ. 8፡6-7/። እሱ የዩኒቨርስ ንጉሥ ሲሆን፣ እነርሱ ደግሞ ሕዝቡን የሚመሩ ናቸው /በምሳሌ/ በእርሱ ሕግ።

መ. አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ /ገጽ 784/ የሚለው ደራሲው ሌዋዊ ዘማሪ እንደ ነበረ ነው፣ እናም መዝሙሩ የተገኘው ከመቅደስ እንደሆነ ነው የሚታሰበው /ማለትም፣ ከእግዚአብሔር ከራሱ/። ይህ ነው እንግዲህ የቃሉን ተለዋዋጭነት የሚያሳየው፣ በእግዚአብሔርና በንጉሥ መካከል።

ሠ. መዝሙሩ የያዘው

1. ተዛማጅ መክፈቻ /ቁ. 1-2/ እና መዝጊያ /ቁ. 16-17/
2. ለንጉሥ የተበረከተ፣ ቁ. 3-9
3. ለሙሽራ የተበረከተ፣ ቁ. 10-15

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 45፡1-2**

**ለመዘምራን አለቃ በመለኮቶች የቆሬ ልጆች ትምህርት የፍቅር መዝሙር።**
**[1]ልቤ መልካም ነገርን አፈለቀ፥**
**እኔ ሥራዬን ለንጉሥ እነግራለሁ**
**አንደበቴ እንደ ፈጣን ጸሓፊ ብርዕ ነው።**
**[2]ውበትህ ከሰው ልጆች ይልቅ ያምራል**
**ሞገስ በከንፈሮችህ ፈሰሰ**
**ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለም ባረከህ።**

**45፡1** ደራሲው ራሱን ለአንባቢዎቹ ያስተዋውቃል /እዚህጋ ብቻ መዝሙር ላይ/ እዚህ ቁጥር ላይ።

1. ልቡ /ማለትም፣ እሱ ራሱ/ ያፈልቃል (ቢዲቢ 935፣ ኬቢ 1222፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፤ LXX "ይፈነዳል" የሚል አለው) መልካም ነገርን /ማለትም፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ንጉሥ በማመስገን/
2. የጻፈው ንጉሡን በጋብቻው ላይ ለማወደስ ነው
3. አንደበቱ እንደ ፈጣን ጸሐፊ ብርዕ ነው /ማለትም፣ [1] እሱ ንጉሡን ለማመስገን ጉጉት ነበረው ወይም [2] እሱ የቤተ መንግሥት ባለቅኔ ወይም ጸሐፊ ይሆናል፣ ዕዝራ 7፡6/

**45፡2** እሱም ንጉሡን በቅኔአዊ ምናብ ምስያ ይገልጻል።

1. እሱ ውብ ነው /ማለትም፣ "እጅግ የተዋበ፣" አየተመት፣ አእቅ፣ አኢመቅ፤ ይህ ቃል [ቢዲቢ 421፣ ኬቢ 421] አልፎ አልፎ ለሰዎች ጥቅም ላይ ይውላል፤ እሱም ያልፎ አልፎ መልክ ነው – *ፓገል* የተጠናቀቀ) ከሌሎች ሰዎች ይልቅ ("የሰው ልጆች")
2. ንግግሩ ያማረ ነው /አእቅ/ ባለ ግርማ ነው (ምሳ. 22:11፤ መክ. 10:12)፤ ቁ. 4ሐ ትይዩ እንደሆነ አስባለሁ
3. ስለዚህ፣ እግዚአብሔር ለዘላለም ይባርክሃል - ስለዚህ ሁለት ሐሳቦች አሉ
   ሀ. በጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/ ግነታዊ፣ ንጉሣዊ ቋንቋ የታወቀ ነው
   ለ. ከሎጂካዊ ሳቢያና ውጤት ተጠንቀቁ /ማለትም፣ ያህዌ ባረከው ባግባቡ ስላከናወነ/። በቅዱስ ቃሉ የሚገኝ ተቃርኖ /ማመዛዘኛ/ አለ፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነትና በሰዎች ነጻ ፍቃድ መካከል /ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 25፡12 ላይ/። መታዘዝ ጠቃሚ ነው ነገር ግን መጠራት ግን ዋነኛ ነው። እሱ ንጉሥ የሆነው ስለሚገባው አይደለም፣ ነገር ግን በቤተ-ሰብ የዘር ሐረግ ነው።

**መዝሙር ፡ 45፡3-5**

**[3]ኃያል ሆይ፥ በቍንጅናህና በውበትህ**
**ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ።**
**[4]ስለ ቅንነትና ስለ የዋህነት ስለ ጽድቅም**
**አቅና ተከናወን ንገሥም**
**ቀኝህም በክብር ይመራሃል።**
**[5]ኃያል ሆይ፥ ፍላጻዎችህ የተሳሉ ናቸው፥**
**እነርሱም በንጉሥ ጠላቶች ልብ ውስጥ ይገባሉ፥**
**አሕዛብም በበታችህ ይወድቃሉ።**

**45፡3-5** ይህ አንጓ ቅኔአዊ ምናባዊ ምስያ ነው፣ ስለ ንጉሥ ወታደራዊ ድል። እሱ ያህዌን እንደሚወክል ተገንዘብ፣ በሚዋጋበት ጊዜ (LXX)

1. "እውነት" /ቢዲቢ 54/
2. "ቅንነት" (ያልተለመደ የአናባቢ አመላካች፣ ቢዲቢ 776፣ ምሳ. 15:33፤ 18:12፤ 22:4፤ ሶፎ. 2:3)

ሦስቱን ተተኳሪዎች እና ሁለቱን ተጽዕኗዊዎች ተገንዘብ፣ ወታደራዊ ምናብ የሚያንጸባርቁትን።

1. "ሰይፍህን በወገብህ ታጠቅ" – ቢዲቢ 291፣ ኬቢ 291፣ *ቃል* ተተኳሪ፣ ቁ. 3፣ ዘዳ. 1:41፤ መሳ. 3:16፤ 18:11፤ 1 ሳሙ.17:39፤ 25:13

2-3. "አቅና፣ ንገሥም" ቁ፣ 4
   ሀ. "ተከናወን!" – ቢዲቢ 852፣ ኬቢ 1026፣ *ቃል* ተተኳሪ
   ለ. "አቅና" – ቢዲቢ 938፣ ኬቢ 1230፣ *ቃል* ተተኳሪ

4. "ቀኝህም ይመራሃል፣" ቁ. 4 – ቢዲቢ 434፣ ኬቢ 436፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
5. "አሕዛብም በበታችህ ይወድቃሉ፣" ቁ. 5– ቢዲቢ 656፣ ኬቢ 709፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

**45:3** "ኃያል" (ቢዲቢ 217 I) እና "ግርማዊ" (ቢዲቢ 214) ዘወትር የሚያያዘው ከእግዚአብሔር ጋር ነው (ማለትም፣ መዝ. 104:1)። አአመመቅ ተውላጠ ስሞቹን እንዴት በትልልቁ ፊደላት እንደጻፋቸው ተገንዘብ፣ 45:2፣3፣4፣5፣6፣7፣8፣9 ላይ። ነገር ግን እነርሱ ለእስራኤል ንጉሥ ደግሞ ጥቅም ላይ ውለዋል (ማለትም፣ መዝ. 21:5)።

▣
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመት** | **"ኃያል ሆይ"** |
| **አእቅ** | **"ኃያል ንጉሥ"** |
| **አኢመቅ** | **"ተዋጊ"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ጀግና"** |
| **የተእመቅ** | **"ተዋጊው ንጉሥ"** |
| **LXX** | **"ኃያል ሆይ"** |

ይህ ቅጽል (ቢዲቢ 150) መሠረታዊ ፍችው "ብርቱ፣" ወይም "ኃያል።" እሱም ጥቅም ላይ የዋለው

1. ለተዋጊ ሰዎች – ዘፍ. 10:9፤ መዝ. 78:65፤ 120:4፤ 127:4፤ መክ. 9:11፤ ማኅልየ ማኅልይ 3:7
2. መሢሕ – ኢሳ. 9:5 (ዳዊት እንደ ዓይነት – መዝ. 89:20)
3. ያህዌ እንደ ታማኝ የኪዳን ተዋጊ /ማለትም፣ ቅዱስ ጦርነት/ – ነህ. 9:32፤ መዝ. 24:8፤ ኢሳ. 10:21፤ ኤር. 32:18

በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ላይ የሚያመለክተው ዳዊታዊ ንጉሥን ነው እንደ ድል አድራጊ ተዋጊ፣ በያህዌ ኃይል እንደታጠቀ።

**45፡4-5** ተውላጠ ስሞቹ ለመለየት አስቸጋሪ ናቸው።

1. አንዳንዶቹ እግዚአብሔርን ያመለክታሉ
2. አንዳንዶቹ ንጉሥን

ይኸው ተመሳሳይ ግርታ ቁጥር 6-7 ላይ አለ። ችግሩ ያለው ደራሲው ንጉሡን የሚገልጸው እንደ ያህዌ እንደ ራሱ ተወካይ አድርጎ መሆኑ ነው። ይኸውም ግልጽ ነው፣ የጥንት ክርስቲያን ደራሲዎች /ማለትም፣ ዕብ. 1፡8-9/ ይሄንን የሚመለከቱት እንደ መሢሐዊ መዝሙር መሆኑ። ለእነርሱ መሢሕ መጥቷል፣ ብኪም የሚያመለክተው ወደ እሱ ነው /ማለትም፣ ኢየሱስ/።

**45:4**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"ድንቅ ነገሮች"** |
| **አየተመት** | **"አስገራሚ ድርጊቶች"** |
| **አእቅ** | **"ታላላቅ ድሎች"** |
| **ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ** | **"ድንቅ ድርጊቶች"** |
| **LXX** | **"በሚያስደንቅ መልኩ"** |

ይህ አንቀጽ (ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ ኒፋል አንቀጽ) ፍችው "አስደናቂ መሳጭ ድርጊቶች" ማለት ነው።

1. እግዚአብሔር ራሱ – ዘዳ. 1:19፤ 7:21፤ 10:20-21
2. የእርሱ ድርጊቶች – 2 ሳሙ. 7:23፤ መዝ. 145:6 (የኤርትራን ባሕር መክፈል፣ መዝ. 106:22)

> ## መዝሙር ፡ 45፡6-9
> **[6]አምላክ ሆይ፥ ዙፋንህ ለዘላለም ነው**
> **የመንግሥትህ በትር የቅንነት በትር ነው።**
> **[7]ጽድቅን ወደድህ ዓመፃንም ጠላህ**
> **ስለዚህ ከባልንጀሮችህ ይልቅ**
> **እግዚአብሔር አምላክ የደስታ ዘይትን ቀባህ።**
> **[8]በልብሶችህ ሁሉ ከርቤና ሽቱ ዝባድም አሉ**
> **ከዝሆን ጥርሶች አዳራሽ ደስ ያሰኙሃል።**
> **[9]የንጉሦች ሴት ልጆች ለክብርህ ናቸው**
> **በወርቅ ልብስ ተጐናጽፋና ተሸፋፍና ንግሥቲቱ በቀኝህ ትቆማለች።**

**45፡6-9** እዚህም ደግሞ አንጓው ሁለቱንም ያህዌንና የእሱን ንጉሣዊ ተወካይ ኅብር ባለው መንገድ ይገልጻል።

**45:6**
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመት፣ LXX** | **"ዙፋንህ፣ አምላክ ሆይ"** |
| **አየተመት ኅዳግ** | **"ዙፋንህ የአምላክ ዙፋን ነው"** |
| **አእቅ** | **"እግዚአብሔር የሰጠህ መንግሥት"** |
| **አኢመቅ** | **"ዙፋንህ ከእግዚአብሔር ነው"** |
| **ጀፒኤስአኤ፣ የተመት** | **"መለኮታዊ ዙፋንህ"** |
| **የተእመቅ** | **"እግዚአብሔር ዙፋን ላይ አስቀመጠህ"** |
| **አእመቅ** | **"ዙፋንህ እንደ እግዚአብሔር ዙፋን ነው"** |

ከትርጉሞች ልዩነት የተነሣ የዕብራይስጡ ጽሑፍ ርግጠኛ አለመሆኑን መመልከት ትችላላችሁ (ጀፒኤስአኤ የግርጌ ማስታወሻ)። በአሀዳዊነት /ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 2፡7 ላይ/ የብኪ ዐውደ-ጽሑፍ ይህ ሊያስረግጥ አይችልም፣ መለኮትን ለንጉሥነት፣ ነገር ግን እሱ

የሚያስረግጠው ንጉሥ ሁሉ የሆነው የመጣውም ከያህዌ ጋር ባለው ግንኙነት ነው። ንጉሥ የያህዌ ምድራዊ ተወካይ ነው፣ ሊቀ ካህን እንደ ሆነው ሁሉ /ዘካርያስ 4/።

የያህዌ ዙፋን (1 ዜና. 29:23፤ ሰቆ. 5:19) ለዘላለም ነው (መዝ. 93:2፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9:5)። የንጉሥ ዙፋን ለዕድሜ ልክ ነው። መሢሑ በተለየ የመጣ ንጉሥ ነው /ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 2፡2 ላይ/። ይህ ሐረግ በብኪ አንድ ፍቺ ነው ያለው፣ እና ሙሉው በአኪ ነው!

**45፡7** አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ይህ ንጉሣዊ ግነታዊ ዘይቤ እንደሆነ ወይም ይህ መዝሙር በርግጥ መልካም ንጉሥን የሚመለከት ለመሆኑ። እሱ አካብን የሚመለከት ከሆነ፣ ንጉሣዊ ግነታዊ ዘይቤ ነው፤ ሰሎሞንን ከሆነ፣ እሱ በመጀመሪያ እውነት ነው፣ ኋላ ላይ ግን አይደለም፤ ዳዊትን ከሆነ በመጀመሪያና በመጨረሻ እውነት ነው፣ ኃጢአት በሠራበት ጊዜ ሳይሆን /ማለትም፣ ቤርሳቤህ፣ ኦርዮ/።

እኛ ዘወትር መጠንቀቅ ይገባናል፣ እግዚአብሔር ስለሚያደርገው በረከት፣ በሰው ልጆች ሥራ ላይ በመመሥረት። እግዚአብሔር ንጉሡን የቀባው ለገዛ ራሱ የመዋጀትና የመገለጥ ዓላማ ነው /ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ/።

አንድ የመጨረሻ ሐሳብ፣ ቁጥር 7 በግልጽ የሚያመለክተው፣ ቁጥር 6 ስለ መለኮት አለማመልከቱን ነው፣ ስለ አንድ የእስራኤል ንጉሥ። ዕብራውያን 1፡8-9 እሱን የሚመለከተው እንደ ዳዊታዊ ንጉሣዊ ዐቢይ ምድብ አድርጎ ነው!

▣ ያህዌ ጽድቅን እንደሚወድ ሁሉ (መዝ. 11:7፤ 33:5)፣ እንዲሁ ደግሞ፣ የእሱም ምድራዊ ተወካይ፣ የእስራኤል ንጉሥ (ማለትም፣ የተቀባው፣ መዝ. 2:2)።

**45:8**
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**
**አየተመት        "ከርቤ"**
**አእቅ፣ አኢመቅ፣**
**የተእመቅ -        ተገድፏል-**

*ቅመሙ* /ቢዲቢ 893 I/ እዚህጋ ብቻ ነው በብኪ የተጠቀሰው። እሱ ምናልባት የቀረፋ ሽቱ የሚጠቅስ ይሆናል።

**45፡9** ይህ ቁጥር የሚያመለክተው በወቅቱ በነበረው ጋብቻ ቀደም ብሎ የነበሩት
1. ንጉሣዊ ሴት ልጆች
2. ሌሎች ሚስቶች/ቊባቶች
3. ንግሥት /ያልተለመደ ቃል፣ ቢዲቢ 993፣ ነህ. 2:6)

## መዝሙር ፡ 45፡10-12

**[10]ልጂ ሆይ፥ ስሚ እዪ ጆሮሽንም አዘንብዪ**
**ወገንሽን ያባትሽንም ቤት እርሺ**
**[11]ንጉሥ ውበትሽን ወድዶአልና፥**
**እርሱ ጌታሽ ነውና።**
**[12]የጢሮስ ሴቶች ልጆች እጅ መንሻን ይዘው ይሰግዱለታል።**
**የምድር ባለጠጎች አሕዛብ በፊትህ ይማለላሉ።**

**45፡10-12** ይህ አንጓ የሚያመለክተው ጋብቻው ከባዕድ ሴት ጋር መሆኑን ነው፣ እሱም የሚገጥመው
1. ዳዊት – ቤርሳቤህ አይሁድ ካልሆነች
2. ሰሎሞን – ከብዙ ባዕድ ሚስቶቹ ጋር (1 ነገ. 11:1-8)
3. አካብ – ኤልዛቤልን ያገባው፣ የጢሮስ ንግሥት (ቁ. 12ን እይ)

**45:10** ይህ ቁጥር አራት ተተኳሪዎች አሉት።
1. ስሚ – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. አተኩሪ ("ተመልከቺ") – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. ጆሮሽን አዘንብዪ – ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ *ሂፊልተተኳሪ*፣ ምሳ. 22:17
4. ወገንሽን እርሺ – ቢዲቢ 1013፣ ኬቢ 1489፣ *ቃል ተተኳሪ*

## መዝሙር ፡ 45፡13-15

**[13]ለሐሴቦን ንጉሥ ልጅ ሁሉ ክብርዋ ነው**
**ልብስዋ የወርቅ መጐናጸፊያ ነው።**
**[14]በኋላዋ ደናግሉን ለንጉሥ ይወስዳሉ፥**
**ባልንጀሮችዋንም ወደ አንተ ያቀርባሉ**
**[15]በደስታና በሐሴት ይወስዱአቸዋል፥**
**ወደ ንጉሥ እልፍኝም ያስገቡአቸዋል።**

**45፡13-15** ይህ የሚያመለክተው የሰርግ ግብዣን ነው፣ ከብዙ ሴቶች ጋር ("ደናግል")። ሌሎች ሚስቶች /ከንግቲቷ ውጭ/ "ሴቶች ልጆች" በመባል ይጠራሉ። (ቁ. 9፣10፣12፣13)።

ይህ አንጓ በቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊ እንዲሆን ተደርጓል፣ እሷን ለማመልከት! ይህም ደግሞ በማጎልየ ማጎልይ ላይ ተደርጓል /የፍቅር ግጥሞች/።

**45:14**

**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"ከውስጥ"**

**ጀፒኤስኦኤ** **"በውስጥ"**

ኤምቲ "ከውስጥ" (הַמָּ፣ ቢዲቢ 819፣ LXX)፣ ነገር ግን አንዳንድ ሊቃውንት የሚያስቡት "ዕንቁ" (פְּנִינִים፣ ቢዲቢ 819፣ ኢዮብ. 28:18፤ ምሳ. 3:15፤ 8:11፤ 31:10፤ ሰቆ. 4:7)።

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ለኤምቲ "ሀ" ደረጃ ይሰጠዋል።

**መዝሙር ፡ 45፡16-17**

**[16]በአባቶችሽ ፋንታ ልጆች ተወለዱልሽ፥**
**በምድርም ሁሉ ላይ ገዥዎች አድርገሽ ትሾሚያቸዋለሽ።**
**[17]ለልጅ ልጅ ሁሉ ስምሽን ያሳስባሉ**
**ስለዚህ ለዓለምና ለዘላለም አሕዛብ ይገዙልሃል።**

**45፡16-17** የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ 429፣ መልካም ማጠቃለያ አለው።

"ባለ ቅኔው ስለ ንጉሡ በመናገር ያጠቃልላል፣ ብዙ ልጆች እንደሚኖሩት ተስፋ በመስጠት፣ እነርሱም እንደእርሱ አባቶች፣ ነገሥታት ሆነው ምድርን ሁሉ እንደሚገዙ።"

ቁጥር 17 የማስረገጫ መንገድ ነው፣ ይህ መዝሙር በረዥም ጊዜ አካባቢ የሚሆን ለመሆኑ፣ እናም በሕይወት ያለ ንጉሥን ማስታወሻ የያዘ ነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ የንጉሣዊ ጋብቻ መዝሙር እንደሆነ ለምን ታሰበ?
2. ቁጥር 6 የሚያመለክተው ስለ እስራኤላዊ ንጉሥ ነውን?
3. ሙሽራዋ ከእስራኤል እንዳልሆነች ለምን ታሰበ?
4. ቁጥር 16-17ን በገዛ ራስህ ቋንቋ ግለጽ።
5. " " ግለጽና አብራራ ዕብራውያን 1:8-9 እንዴት እንደተጠቀመበት።
6. ይህ መዝሙር ለምን መሢሐዊ ተብሎ ታሰበ?

# መዝሙር 46
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር የሕዝቡ መጠጊያ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ። የቆሬ ልጆች መዝሙር፣ ለአላሞዝ የተደራጀ። መዝሙር | እግዚአብሔር የሕዝቡ መጠጊያና የአሕዛብ ድል አድራጊ | የጽዮን መዝሙር የአምላክን አጠቃላይ ድል በአሕዛብ ላይ ለማክበር | እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው | እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው |
| 46:1-3 | 46:1-3 | 46:1-3 | 46:1-3 | 46:1-3ለ |
| | | | | 46:3ሐ |
| 46:4-7 | 46:4-6 | 46:4-7 | 46:4-6 | 46:4-6 |
| | 46:7 | | 46:7 | 46:7 |
| 46:8-11 | 46:8-9 | 46:8-11 | 46:8-10 | 46:8-10 |
| | 46:10 | | | |
| | 46:11 | | 46:11 | 46:11 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር ቅዱስ ቃላዊ ተመስጦ ነው ለማርቲን ሉተር ውዳሴ፣ "ብርቱ ምሽግ ነው አምላካችን።"

ለ. የሚታወቅ ታሪካዊ መቼት የለውም።

ሐ. እግዚአብሔር ሁለቱንም ነው
1. መጠጊያ ምሽግ /ዝከ. ቁ. 7፣ 11/
2. ተዋጊ እሱም በምድር ሁሉ ላይ ጦርነት እንዲያቆም የሚያደርግ /ዝከ. ቁ. 9/

ሆኖም፣ ታላቁ በረከት የሚሆነው ኃይሉ አይደለም፣ ነገር ግን
1. የእርሱ መገኘት
2. የእርሱ ሁለንተናዊ ዓላማ /ዝከ. ቁ. 10፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ፣ መዝሙር 2 መግቢያ ላይ/

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 46፡1-3**
**ለመዘምራን አለቃ ስለ ምሥጢር የቆሬ ልጆች መዝሙር።**
**[1]አምላካችን መጠጊያችንና ኃይላችን፥**
**ባገኘን በታላቅ መከራም ረዳታችን ነው።**

> **[2]ስለዚህ ምድር ብትነዋወጥ፥**
> **ተራሮችም ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ አንፈራም።**
> **[3]ውኆቻቸው ጮኹ ተናወጡም፥**
> **ተራሮችም ከኃይሉ የተነሣ ተናወጡ።      ሴላህ።**

**46፡1 "አምላክ"** ሁለተኛው የመዝሙር መጽሐፍ ኤሎሂምን ይጠቀማል፣ ከያህዌ ይልቅ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ የመለኮት ስሞች፣ መዝ. 1፡1 ላይ።

▣ ***"መጠጊያችንና ኃይላችን"*** እነዚህ ተዘውታሪ የእግዚአብሔር መግለጫዎች ናቸው (መዝ. 14:6፤ 18:1-2፤ 40:17፤ 62:7-8፤ 142:5)።

**46፡2-3** የመዝሙረኛው እምነት ያስረግጣል (ማለትም፣ "አልፈራም፣" መዝ. 23:4፤ 27:1) በብዙ ችግር መካከል እያለ።

1. ምንም እንኳ ምድር ብትነዋወጥ
2. ምንም እንኳ ተራሮች ወደ ባሕር ልብ ቢወሰዱ
3. ውኆቻቸው ቢጮኹ /ቢዲቢ 242፣ ሀመ ) እና ቢናወጡ (ቢዲቢ 330 ፣ ገመበ፣ የድምጽ መቀያር)
4. ተራሮችም ከኃይሉ የተነሣ ቢናወጡ

እንደዚህ ዓይነቶቹ የጥፋት ሁነቶች ሊያመለክቱ የሚችሉት

1. ያህዌ ወደ ፍጥረቱ ሲቀርብ ምን እንደሚሆን /ማለትም፣ "ይቀልጣል፣" መዝ. 46:6ለ፤ 98:7-9፤ ሚኪያስ 1:4)
2. የችግር ዘይቤ (ማለትም፣ "የውጥረት ስፍራዎች፣" ቢዲቢ 865 ፣ አንስታይ ስም፣ ዘዳ. 31:17፣21፤ 1 ሳሙ.10:19፤ መዝ. 71:20፤ ምሳ. 1:27)

**46፡3** ይህ ቁጥር ሦስት ያልተጠናቀቁ አሉት /ማለትም፣ በሂደት ላይ ያለ ድርጊት/።

1. የውኃዎች ጩኸት – ቢዲቢ 242፣ ኬቢ 250፣ *ቃል*
2. የውኃዎች ፏፏቴ – ቢዲቢ 330፣ ኬቢ 330፣ *ቃል*
3. ተራሮችም ተናወጡ – ቢዲቢ 950፣ ኬቢ 1271፣ *ቃል*

የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 1333) የሚለው "ይህ አፈ-ታሪካዊ ቋንቋ ነው ወደ ከነአናውያን ባህል ተመልሶ የሚሄድ ነው። እነዚህ አፈ-ታሪኮች ከመገኘታቸው በፊት፣ መዝሙር ዘወትር ይያያዝ የነበረው ከፍጻሜው ጦርነት ጋር ነበር /ራሺ እና ራዳክ/።"

መልኅቅ መጽሐፍ ቅዱስ /ኤቢ/ መዝሙር ላይ በሚትቼል ዳሆድ፣ የራስ ሻምራን ሥነ-ጽሑፍ ተጠቅሟል፣ ዑጋሪት ላይ የተገኘውን፣ የዕብራይስጥ ቅኔን ለማብራራት፣ የመዝሙር መልክ ያለውን። እነዚህ ዑጋሪታዊ ጽሑፎች ቅኔዎች ናቸው፣ ስለ በአል እና የከነዓን ጣዖታት። እስራኤል ዘወትር ይወስዳሉ፣ የአሕዛብ መጠሪያዎችን፣ ምስያዎችን፣ እና አፈ-ታሪኮችን፣ እናም ለውጠዋቸው የኪዳን አምላካቸውን፣ ያህዌን፣ አንዱን እውነተኛ አምላክ ለማመስገን /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት /አንድ አምላክ/ መዝ. 2፡7 ላይ!

▣ **"ሴላህ"** *ቃሉ መዝሙሩን ወደ ሦስት አንጓዎች ይከፍለዋል።*

1. ቁ. 1-3
2. ቁ. 4-7
3. ቁ. 8-11

ለታሳቢ ፍቺ መዝ. 3፡2 ላይ ማስታወሻውንና መግቢያ ለመዝሙር፣ VIII ተመልከት።

> ***መዝሙር ፡ 46፡4-7***
> **[4]የወንዝ ፈሳሾች የእግዚአብሔርን ከተማ ደስ ያሰኛሉ**
> **ልዑል ማደሪያውን ቀደሰ።**
> **[5]እግዚአብሔር በመካከልዋ ነው አትናወጥም፥**
> **እግዚአብሔርም ፈጥኖ ይረዳታል።**
> **[6]አሕዛብ ተናወጡ መንግሥታትም ተመለሱ**
> **እርሱ ቃሉን ሰጠ፥ ምድርም ተንቀጠቀጠች።**
> **[7]የሠራዊት ጌታ ከእኛ ጋር ነው**
> **የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው።      ሴላህ**

**46፡4-7** ይህ አንጓ የሚገልጸው እግዚአብሔርን የከበበውን ጸጥ ያለ ሰላም ነው፣ ምድር በብርቱ ነውጥ ላይ በሆነችበት ጊዜ /ማለትም፣ ራዕይ 4-5/።

1. ሳያቋርጥ የሚፈስስ ወንዝ ("የመስኖ ቦይ፣" ቢዲቢ 625፣ መዝ. 36:8፤ 65:9፤ ሕዝ. 47:1፤ ኢዩኤል 3:18፤ ዘካ. 14:8፤ ራዕ. 22:1፣ 17) በ"እግዚአብሔር ከተማ" (መዝ. 48:1፣8፤ 87:3፤ 101:8፤ ኢሳ. 60:14፤ ራዕ. 3:12)
2. የእግዚአብሔር ከተማ አትናጥም (ማለትም፣ አትንቀጠቀጥም) ያህዌ በመካከሏ ስለሆነ (ሆሴ. 11:9፤ ዘካ. 2:5፤ ዕብ. 11:10፤ 12:22፤ 13:14)
3. እግዚአብሔር ይረዳታል ኢሳ. 41:14) በማለዳ ፈጥኖ (ፍጹም ለሆነ ሰዓት ምስያ፣ መዝ. 5:3፤ 17:15፤ 30:5፤ 90:14)። ይህ "ዕርዳታ" የሚያያዘው "አሕዛብ ተናወጡ" ከሚለው ጋር ነው ቁ. 6ሀ (ተመሳሳይ ግሥ ከቁ. 3ሀ መዝሙር 2)። "አሕዛብ" በድጋሚ ተጠቅሷል፣ ቁ. 10ለ ላይ። የእግዚአብሔር ዓላማ ሁልጊዜ አሕዛብን ያካትታል /ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ/!
4. የእግዚአብሔር ከተማ አትናወጥም /ማለትም፣ የጽናትና የቀጣይነት ምስያ/

**46:4ለ**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ ጄፒኤስአኤ** | **"ቅዱስ ማደሪያ ስፍራዎች"** |
| **አኪጀት** | **"በመቅደሱ በቅዱስ ስፍራ"** |
| **አየተመት** | **"ቅዱስ ማደሪያው"** |
| **አእቅ** | **"የተቀደሰ ቤቱ"** |
| **አኢመቅ** | **"ማደሪያውን ቀደሰ"** |
| **LXX** | **"ስፍራውን ቀደሰ"** |
| **የተእመቅ** | **"ቅዱስ ማደሪያ"** |

ኤምቲ (ቢ.ዲ.ቢ. 1015) አለው

1. መቅደስ – ዘጸ. 25:9፤ 26:30፤ 38:21፤ ዘኍ. 9:18፣22፤ 40:34-35 (ማለትም፣ "የመገናኛ ድንኳን")፤ መዝ. 78:60
2. ማደሪያ ስፍራ
   ሀ. የቆሬ (ማለትም፣ ድንኳኖች) – ዘኍ. 16:24፣27
   ለ. ያዕቆብ – መዝ. 87:2
   ሐ. የያህዌ (ማለትም፣ መቅደስ) – መዝ. 26:8፤ 74:7
   መ. የያህዌ (ግን የብዙ፣ ማለትም፣ በመቅደሱ ዙሪያ ያሉት ግንባታዎች) – መዝ. 43:3፤ 84:1፤ 132:5፣7፤ ሕዝ. 32:27

የብዙ ቁጥሩ የሚያሳየው

1. በመቅደሱ ያሉትን ግንባታዎች ሁሉ
2. የግርማውን ብዛት /ማለትም፣ እጅግ የተቀደሰ/

ከትርጉሞች መመልከት ትችላላችሁ፣ አንዳንዶች "ቅዱስ"ን እንደቀየሩት (ቅጽል፣ ቢ.ዲ.ቢ. 872) "መቀደስ" ወደሚለው ግሥ (LXX፣ ቫልጌት፣ አኢመቅ)፣ እሱም የአናባቢ ለውጥ ብቻ የሆነ።

▣ **"ልዑሉ"** ይህ የመለኮት መጠሪያ ነው (ኤሊኦን፣ ቢ.ዲ.ቢ. 751 II፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:1 ላይ) እሱም ዘፍ. 14:18-22፤ ዘኍ. 24:15፤ እና ዘዳ. 32:8፣ ላይ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ነገር ግን ባብዛኛው (16 ጊዜ) መዝሙር ላይ፣ ዳንኤል 7 ላይ (4 ጊዜ)፡ መሠረታዊ ፍችው "ከፍ ያለ" ነው። እሱም ባብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውለው እስራኤላውያን ባልሆኑ ነው።

**46፡6** ተቃርኖውን ተገንዘቡ፣ በመካከል ያለውን

1. አሕዛብ ተናወጡ፣ ቁ. 6ሀ /ውጤታማ ያልሆነ/
2. የያህዌ ድምጽ፣ ቁ. 6ለ /ውጤታማ/

"ቀለጡ" የሚለው ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 556፣ ኬቢ. 555፣ ቃል ያልተጠናቀቀ) ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፣

1. በዘይቤነት ለጠላት ብርታት – ዘጸ. 15:15፤ ኢያ. 2:9፣11፣24፤ ኢሳ 14:31
2. በዘይቤነት ለፍርድ – አሞጽ 9:5
3. በጥሬው (ማለትም፣ የምድር የመጨረሻ ማጽዳት) – 2 ጴጥ. 3:10

**46:7** ይሄው ተመሳሳይ ተስፋ፣

1. የሠራዊት ጌታ ከእኛ ጋር ነው (መዝ. 24:10፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት: የመለኮት ስሞች መዝ. 1:1፣ ዘኍ. 14:9፤ 2 ዜና. 13:12)
2. የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው (መዝ. 9:9፤ 48:3፤ 59:9፣16፣17)

ቁጥር 11 ላይ ተደግሟል፣ ለአጽንዖት! እነዚህ መግለጫዎች የመዝሙረኛው ተስፋ እና ያህዌ ለሕዝቡ የገባው ቃል ናቸው።

▣ **"ከእኛ ጋር ነው"** ይህ ታላቁ ተስፋ ነው (ዘኍ. 14:9፤ 11 ዜና. 13:12፤ መዝ. 9:10፤ 37:28፤ 94:14፤ ዕብ. 13:5 [ከዘዳ. 31:6፤ ኢያ. 1:5])። እግዚአብሔር ያስፈልገናል!

## መዝሙር ፡ 46፡8-11

**8 የእግዚአብሔርን ሥራ፥**
**በምድር ያደረገውንም ተአምራት እንድታዩ ኑ።**
**9 እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ጦርነት ይሽራል።**
**ቀስትን ይሰብራል፥ ጦርንም ይቈርጣል**
**በእሳትም ጋሻን ያቃጥላል።**
**10 ዕረፉ፥ እኔም አምላክ እንደ ሆንሁ እወቁ**
**በአሕዛብ ዘንድ ከፍ ከፍ እላለሁ፥ በምድርም ላይ ከፍ ከፍ እላለሁ።**
**11 የሠራዊት ጌታ ከእኛ ጋር ነው**
**የያዕቆብ አምላክ መጠጊያችን ነው። ሴላህ።**

**46፡8-11** ይህ አንዱ የእግዚአብሔርን ዓላማ ይገልጻል። ሁለቱን የቁጥር 8 ተተኳሪዎች እና የቁጥር 10 ትይዩዎችን ተገንዘብ።

1. ኑ – ቢ.ዲ.ቢ. 229፣ ኬቢ. 246፣ ቃል ተተኳሪ፣ ቁ. 8
2. እነሆ ("እዩ") – ቢ.ዲ.ቢ. 302፣ ኬቢ. 301፣ ቃል ተተኳሪ፣ ቁ. 8፣ ኢዮብ 23:9፤ መዝ. 63:2፤ Isa. 26:11፤ 33:17፣20፤ 48:6
3. ያስቆማል (ያህዌ ይናገራል ቁ. 10 ላይ) – ቢ.ዲ.ቢ. 951፣ ኬቢ. 1276፣ ሂፊልተተኳሪ፣ ቁ. 10 (ማለትም፣ በዐውደ-ጽሑፍ ጦርነትን እንዲያቆም ለዓለም የተደረገ ጥሪ/
4. እወቁ – ቢ.ዲ.ቢ. 393፣ ኬቢ. 390፣ ቃል ተተኳሪ፣ ቁ. 10 (ማለትም፣ የያህዌ ኃይልና ማዳን፤ ይህ ከሥነ-መለኮት አኳያ ከቁ. 2 ጋር ትይዩ ነው2)

ያህዌ ጦርነት ሁሉ እስከ ምድር ዳርቻ እንዲቆም አዟል! አዲስ ቀን እየመጣ ነው (ማለትም፣ የሰላም አለቃ፣ ኢሳ. 9:6፤ 66:12፤ ዮሐንስ 14:27፤ 16:33፤ 20:19)። ለመሐሪው የፍጥረት አምላክ ክብር የሚሰጥበት ቀን። አሕዛብ ሁሉ እውቅና ይሰጡታል (ኢሳ. 2:2-4፤ 25:6-9፤ 56:6-8፤ ኤፌ. 2:11-3:13)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ሁለንተናዊ የመዋጀት ዕቅድ፣ ከመዝሙር 2 መግቢያ ላይ።

**46፡8 "ውድመት"** አእቅ "እግዚአብሔር ያደረገውን ኑ ተመልከቱ። በምድር ላይ ያደረገውን አስደናቂ ነገር ተመልከቱ" የሚል አለው። "ውድመት" የሚለው ቃል /ቢ.ዲ.ቢ. 1031 l/ መዝሙር ላይ ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል /እዚህጋና 73፡19 ላይ/፣ እዚያም ውድመትን በመግለጽ። የዘጸአት ሁነቶች "አስደናቂ ነገሮች" በመባል ይጠራሉ /ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9፡1 ላይ/፣ ወታደራዊ ውድመት ባሕርዩ እንደዚያ ነው። ቃሉ አዘውትሮ የሚከሰተው ኤርምያስ ላይ ነው /24 ጊዜ/ እናም ሁሉም የሚገልጹት ውድመትን፣ ጥፋትን፣ ሽብርን፣ መፍረስን ነው። ባጠቃላይ ያህዌ ጦርነትን ያቆማል፣ የአሕዛብን ወታደራዊ ኃይል ድል በማድረግ /ዝከ. ቁ. 9፤ መዝሙር 2/።

**46:9**
***አአመመቅ፣ አኪጀት*** ***"ሠረገላዎች"***
***አየተመት፣ አእቅ፣***
***አኢመቅ፣ የተእመቅ፣***
**LXX** ***"ጋሻዎች"***
**ጀፒኤስአኤ** ***"ጋሪዎች"***
የዕብራይስጡ የግሥ ሥር ርግጠኝነት የለውም
1. "ክብ" – ቢ.ዲ.ቢ. 222፣ לגע לוגע (DSS፣ "ክብ ጋሻ፣" 1ኪውኤም6:15)
2. "ተሽከርካሪ ጋሪ" – ቢ.ዲ.ቢ. 722፣ הלגע (በኤምቲ ላይ እንደ ጦርነት ሠረገላ ፈጽሞ የለም)
በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ "ክብ ጋሻ" በተሻለ የሚገጥም ይሆናል።

**46፡11** ትይዩው ዓለም አቀፋዊ አጽንዖት ይዟል! አስደናቂዋ ከተማ ለሁሉም ነች /ማለትም፣ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም፣ ራዕይ 21-22!/
ለ"መሬት" (46:2፣6፣8፣9፣10) ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 1:2 ላይ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ቁጥር 2-3 ላይ ያው ምስያ ከፍጻሜ ዘመን ሁነቶች ነው ወይስ ከከነአን አፈ-ታሪክ?
2. ከእግዚአብሔር ከተማ የሚፈሰውን ወንዝ ጠቀሜታ አብራራ።
3. ቁጥር 6 እንዴት መዝሙር 2ን ይመስላል?
4. ቁጥር 10 ላይ ያህዌ የሚናገረው ለማነው?
5. ቁጥር 10 ስለ አሕዛብ ሽንፈት ነው ወይስ አሕዛብ ወደ እግዚአብሔር ሕዝብ ስለመካተታቸው?

## መዝሙር 47
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር የምድር ንጉሥ<br>ኤምቲ መግቢያ መዝሙር፤<br>የቆሬ ልጆች መዝሙር። | ምስጋና ለእግዚአብሔር፣ ለምድር ገዥ | ውዳሴ ለእግዚአብሔር ንጉሥነት<br>የንግሥና በዓል ለማክበር፣ በአሕዛብ<br>ሁሉ ላይ | ሉዓላዊው ገዥ | ያህዌ፣ የእስራኤል ንጉሥ፣<br>የምድር ንጉሥ |
| 4:1-4 | 47:1-4 | 47:1-4 | 47:1-4 | 47:1 |
| | | | | 47:2-3 |
| | | | | 47:4 |
| 47:5-9 | 47:5-7 | 47:5-7 | 47:5-7 | 47:5 |
| | | | | 47:6 |
| | | | | 47:7-8 |
| | 47:8-9 | 47:8-9 | 47:8-9 | |
| | | | | 47:9 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ሦስተኛው አንቀጽ*
4. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የሚያተኩረው ሁለንተናዊውን የፈጣሪ/የሚዋጅ አምላክ ልዕልና ነው። እግዚአብሔር ይገዛል (መዝ. 93:1፤ 96:10፤ 97:1፤ 99:1፤ ኢሳ. 52:7)!

ለ. የዚህ ንጉሣዊ ማስረገጫ እንዴትና መቼው ርግጠኝነት የለውም።
1. የዳዊታዊ ንግሥና በእስራኤል ላይ ዓመታዊ ክብረ-በዓል ይወከላል
2. የፍጻሜ ዘመን የሁሉም ነገሮች ማክተም /1 ቆሮ. 15፡25-27/
3. እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ያለው ስፍራ ተገቢ የሆነ ሥነ-መለኮት (ማለትም፣ አሀዳዊነት [ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 2:7 ላይ]፣ እሱ ሁሌም ዘወትርም ገዝቷል፣ ይገዛልም)

ሐ. የመዝሙሩ ሁለንተናዊ ይዘቶች ብርቱ አመላካች ናቸው፣ እግዚአብሔር የዩቨርስ ፈጣሪና ንጉሥ ለመሆኑ።
1. ሰዎች ሁሉ፣ ቁ. 1
2. ታላቁ ንጉሥ በምድር ሁሉ ላይ፣ ቁ. 2ለ
3. ሕዝቦችን ይገዛል... አሕዛብን፣ ቁ. 3
4. እግዚአብሔር በአሕዛብ ላይ ይገዛል፣ ቁ. 8 (መዝ. 22:28፤ 1 ቆሮ. 16:31)
5. የሕዝብ መኳንንት /የተከበሩ/ /ማለትም፣ እስራኤል ሳይሆን፣ ግን አሕዛብ/ ራሳቸውን ይሰበስባሉ፣ ቁ. 9
6. የምድር ጋሻዎች የእግዚአብሔር ናቸው፣ ቁ. 9
7. *የኤሊዮን አጠቃቀም ሊሆን ይችላል፣* እሱም የተለመደ መጠሪያ፣ ለልዕለ አማልክት፣ ለጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/፣ እሱም ያህዌ በሌሎች አማልክት ሁሉ ላይ ያለውን ገዥነት ያመለክታል /ጣዖታት፣ ኤሎሂምስ፣ መላእክት፣ ወዘተ/

**መዝሙር ፡ 47፡1-4**

[1]አሕዛብ ሁላችሁ፥ እጆቻችሁን አጨብጭቡ፥
በደስታ ቃልም ለእግዚአብሔር እልል በሉ።
[2]እግዚአብሔር ልዑል ግሩምም ነውና፥
በምድር ሁሉ ላይም ታላቅ ንጉሥ ነውና።
[3]አሕዛብን ከእኛ በታች፥
ወገኖችንም ከእግራችን በታች አስገዛልን።
[4]ለርስቱ እኛን መረጠን፥
የወደደውን የያዕቆብን ውበት። ሴላህ።

**47፡1-2** የመለኮት ስሞችን ተገንዘብ።

1. እግዚአብሔር – *ኤሎሂም፣* ቁ. 1፣ 5፣ 6፣ 8 (ሁለቴ)፣ 10
2. ጌታ – *ያህዌ*፣ ቁ. 2
3. ልዑሉ – *ኤሊኦን*፣ ቁ. 2 (የተለመደ ስም ለልዕለ-አምላክ፣ በጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/ ዘፍ. 14፡18-20፣23፤ ዘኍ. 24፡15፤ ዘዳ. 32፡8-9)
4. ንጉሥ – ቁ. 2፣ 6፣ 8 ("ይነግሣል፣" ዘካ. 14፡9፤ ሚል. 1፡14)
5. የአብርሃም አምላክ – ቁ. 10 (ማለትም፣ የኤሎሂም ነጠላ መልክ፣ ዘዳ. 32፡15፣17፤ መዝ. 18፡22)

ቅኔ ዘወትር ለእስራኤል አምላክ ብዙ ስሞችን ይጠቀማል። እሱም ዘወትር ስሞችንና መግለጫዎችን ይወስዳል፣ ከሌሎች ባህሎች፣ እናም ለእስራኤል አምላክ ይጠቀምባቸዋል። ሁለተኛው የመዝሙር መጽሐፍ በዋነኛነት ኤሎሂምን ይጠቀማል።

**47፡1** ይህ መዝሙር በሁለት ተተኳሪዎች ይጀምራል፣ ምድርን በማሳሰብ /ማለትም፣ "ሰዎችን ሁሉ"/ ድምጻቸውን ከፍ አድርገው እንዲደሰቱ።

1. "እጃችሁን አጨብጭቡ" – ቢዲቢ 1075፣ ኬቢ 1785፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. ለእግዚአብሔር እልል በሉ – ቢዲቢ 929፣ ኬቢ 1206፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
3. የጦርነት ጩኸት – ዘኍ. 10፡9፤ ኢያ. 6፡20፤ ኢሳ. 42፡13፤ 2 ዜና. 13፡15
4. ጉባኤ – ዘኍ. 10፡7
5. ድል – ኤር. 50፡15፤ ሰፉ. 3፡14
6. ማስረገጫ – 1 ሳሙ.10፡24፤ መዝ. 47፡1፤ 66፡1፤ 81፡1፤ 95፡1-2፤ 98፡4፤ 100፡1፤ ዘካ. 9፡9
7. ሃይማኖታዊ ደስታ – 1 ሳሙ. 4፡5፤ ዕዝራ 3፡11፣13
8. መከራ – ኢሳ. 15፡4፤ ሚኪያስ 4፡9

**47፡2 "ባለ ግርማ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ *ኒፋል አንቀጽ*) የሚገልጸው

1. እስራኤል አቋርጠው ያለፉበት ምድረ-በዳ፣ ዘጸአት ላይ፣ ዘዳ. 1፡19፤ 8፡15
2. መደነቅን የሚፈጥር – መዝ. 47፡2፤ 68፡35፤ 76፡8
3. የሚመስጥ አክብሮት – ዘዳ. 7፡21፤ 10፡17፤ ነህ. 1፡5፤ 9፡32፤ ዳን. 9፡4

ቁጥር 2 እና 3 እጅግ ተመሳሳይ ናቸው፣ በፍች። እሱ ብቸኛው ነው፣ ብቸኛው፣ እኛም ኃጢአተኛ ፍጡራን ነን! እሱ ግን ከእኛ ጋር ኅብረት ማድረግን መረጠ!

▣ **"በምድር ሁሉ ላይ"** ተደጋጋሚ የሆነ ሞላ-ምድራዊ አጽንዖት ያለ ይመስላል፣ መዝሙር 45-50 ላይ 45-50 (ዝከ. ቁ. 1፣ 7-9፣ መዝ. 45፡16፤ 46፡10፤ 47፡2፤ 48፡2፣10፤ 49፡1፤ 50፡1፣4፣12)። ይህ ጭብጥ "ምናልባት" እነዚህ መዝሙራት ለምን አንድ ላይ እንደተቀመጡ ይሆናል። ደግሞም መዝሙር 96-99 ተመልከት።

ምድር የጌታ ናት (ዘጸ. 9፡29፤ 19፡5)። እሱ ፈጣሪ ነው፣ መጋቢ (ማለትም፣ *ኤሎሂም*፣ ዘፍጥረት 1)፣ እና የኪዳን አምላክ (ማለትም፣ *ያህዌ*፣ ዘፍ. 2፡4)። ሌላ የለም (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት /አንድ አምላክ/ መዝ. 2፡7 ላይ)!

**47፡3-4** እነዚህ ቁጥሮች አጽንዖት የሚሰጡት የእስራኤልን መመረጥ ነው፣ እንደ ያህዌ የተለየ የኪዳን ሕዝብ (ዘፍ. 12፡1-3፤ ዘጸ. 19፡5-6)። እስራኤል ማለት ለአሕዛብ ብርሃን እንድትሆን ነበር፣ ነገር ግን አልሆነላትም (ሕዝ. 36፡22-23፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ፣ መዝ 2 መግቢያ ላይ/።

የእስራኤል ወታደራዊ ድሎች የያህዌ ድሎች ነበሩ (ማለትም፣ ቅዱስ ጦርነት)።

**47፡4 "ርስት"** በተስፋይቱ ምድር ክፍፍል ላይ /ማለትም፣ ኢያሱ 12-19/ ሌዋውያን መሬት አልተሰጣቸውም ነበር /ማለት ግን፣ 48 ከተሞች፣ ኢያሱ 20-21/። እንደተባለ፣ "ያህዌ ርስታቸው ነው።" ይህ አስደናቂ ተስፋ ለእስራኤል ሁሉ እንዲሆን ተስፋፍቷል፣ ብሎም 1 ጴጥ. 1፡4 ላይ ለአማኞች ሁሉ እንዲሆን!

ይህን ደግሞ መመልከት ይቻላል፣ ከነአንን እንደሚያመለክት (ማለትም፣ የተስፋይቱ ምድር፣ ዘፍ. 12፡7፤ 15፡12-21፤ 17፡8፤ ዘጸ. 3፡8፤ ዘዳ. 1፡8)። ይኸውም "ርስት" እና "ክብር (ቢዲቢ 144) የያዕቆብ" ትይዩ ናቸው። ይሄንን ለማጽናት የእኔ እምቢተኝነት፣ የመዝሙሩ ሁለንተናዊ አጽንዖት ነው። ምድር፣ ከነአን ብቻ ሳይሆን፣ የጌታ ነው!

▣ **"የወደደውን"** ብኪ. ላይ እስራኤል ማዕከላዊ ስፍራ ነበረው፣ ነገር ግን አኪ. ላይ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል ማዕከላዊ ስፍራ ይኖረዋል (ዮሐንስ 3፡16፤ 4:42፤ 1 ጢሞ. 2:4፤ 4:10፤ 1 ዮሐንስ 2:1-2፤ 4:14)። ክርስቲያኖች ብኪን መመልከት/መተርጎም የሚኖርባቸው በአኪ. እይታ አንጻር ነው፣ በተገላቢጦሹ ሳይሆን!

▣ **"ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 3፡2 ላይ እና መግቢያ ለመዝሙር፣ VII

**መዝሙር ፡ 47፡5-9**

**[5]አምላክ በእልልታ፥**
**እግዚአብሔር በመለከት ድምፅ ዐረገ።**
**[6]ዘምሩ፥ ለአምላካችን ዘምሩ**
**ዘምሩ፥ ለንጉሣችን ዘምሩ።**
**[7]እግዚአብሔር ለምድር ሁሉ ንጉሥ ነውና**
**በማስተዋል ዘምሩ።**
**[8]እግዚአብሔር በአሕዛብ ላይ ነገሠ**
**እግዚአብሔር በቅድስናው ዙፋን ይቀመጣል።**
**[9]የምድር ኃይለኞች ለእግዚአብሔር ናቸውና**
**የአሕዛብ አለቆች ወደ አብርሃም አምላክ ተሰበሰቡ**
**እርሱንም ከፍ ከፍ አደረጉት።**

**47፡5-9** ይህ አንጓ የሚያተኩረው ለእግዚአብሔር ምስጋና ነው። ለድምጽ ቃና ማጽኛ የሆኑትን ቃላት ተገንዘብ።

1. በዕልልታ፣ ቁ. 5
2. በመለከት ድምጽ፣ ቁ. 5

3-7. ምስጋና ዘምሩ፣ ቁ. 6-7 – ቢዲቢ. 274፣ ኬቢ. 273፣ ፔል ተተኳሪ፣ 5 ጊዜ

ብዙ ሊቃውንት 47፡5-8ን የሚመለከቱት እንደ ዓመታዊ ሁነት መግለጫ ነው፣ የእስራኤል ንጉሥ ዙፋን ላይ ሲወጣ፣ እንደ ያህዌ ተምሳሌታዊ ተወካይ፣ ለሁለንተናዊ አገዛዙ /ማለትም፣ ታቦቱ ተመልሶ ወደ መቅደሱ ሲመጣ ለዑደት በኋላ፣ 2 ሳሙ. 6፡15/። ምንም እንኳ ይህ ንድፈ-ሐሳብ ማራኪ ቢሆንም፣ ጥቂት ታሪካዊ ማስረጃ ነው ያለው።

**47፡5 "መለከት"** ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ በእስራኤል ጥቅም ላይ የሚውሉ ቀንዶች

በዕብራይስጥ አራት ቃላት አሉ ከቀንድ/መለከት ጋር የተያያዙ፡

1. "የበግ ቀንድ" (ቢዲቢ. 901) - ወደ ድምጽ መሣርያነት የተቀየረ፣ ኢያ. 6፡5። ተመሳሳይ የሆነ ቃል፣ በቀንዱ የተያዘ፣ እሱንም አብርሃም በይስሐቅ የቀየረው ዘፍ. 22፡13 ላይ።
2. "መለከት" (ቢዲቢ. 1051) - ከሶርያ ቃል ለዱር በግ (አይቤክስ)። ይህ ቀንድ እሱም ዘጸ. 19፡16፣19 ሲና/ኮሬብ ተራራ ጥቅም ላይ የዋለው ነው። ቁ. 1 እና ቁ. 2 ከኢያ. 6፡5 ጋር ትይዩ ነው። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው የአምልኮ ጊዜንና የውጊያ ጊዜን ለማጣጣም ነው (ማለትም፣ ኢያሪኮ ሁለቱም ነበር፣ ዝከ. 6፡4)።
3. "የበግ ቀንድ" (ቢዲቢ. 385) - ከፊንቂያውያን ቃል ለበግ (ዝከ. 6፡4፣6፣8፣13)። እሱም ደግሞ ለኢዩቤልዩ ዓመት ይቆማል ሌዋ. 25፡13፣28፣40፣50፣52፣54፤ 27፡17፣18፣23፣24)።

(እነዚህ ሦስቱ ሁሉ ሲለዋወጡ ይታያሉ ምንም ዓይነት ልዩነት ሳይደረግባቸው። ሚሽናህ (RH 3.2) የማንኛውም እንስሳ ቀንድ — በግ፣ ፍየል፣ ወይም አጋዘን፣እንዲሆን ይፈቅዳል፣ የላም ግን አይሆንም።)

4. "መለከቶች" (ቢዲቢ. 348) - ሊሆን የሚችለው "መዘርጋት፣" ከሚለው ግሥ ነው፣ እሱም ቀጥ ያለ አጥንት (እንደ እንስሳ ቀንዶች ያልተጣመመ)። እነዚህ የተበጁት ከብር ነው (እንደ ግብፅ ቅርጽና መልክ ያለ)። እነዚህ ጥቅም ላይ የሚውሉት፡
   ሀ. ከአምልኮ ሥርዓት ጋር (ዘኊ. 10፡2፣8፣10)
   ለ. ለወታደራዊ አገልግሎት (ዘኊ.10:9፤ 31:6፤ ሆሴዕ 5:8፤ ዕዝራ 3:10፤ ነህ. 12:35፣41)
   ሐ. ለንጉሣዊ ተግባራት (2ነገ. 11፡14)

ከእነዚህ አንደኛው የብረት ቀንድ በቲቶ ቅስት ሮም ላይ ተጠቅሷል፤ ጆሴፈስም *Antiq.* 3.12.6. ላይ ጠቅሷቸዋል።

**47፡7**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"የጥበብ ዝማሬ"** |
| **አኪጀት** | **"በማስተዋል"** |
| **አየተመት** | **"በዝማሬ"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ውዳሴ"** |
| **የተእመቅ** | **"በጥበባችሁ ሁሉ"** |

ቃሉ /ቢዲቢ 968/ በኤምቲ ጥቅም ላይ የዋለው ለአስራ ሦስት መዝሙራት ርዕሶች ነው፣ ነገር ግን እዚህጋ ብቻ የመዝሙር ጽሑፍ ሆኖአል። ቢዲቢ የሚለው እሱ "የምልጃ /የመስጠት/ ግጥም" መሆኑን ነው፤ ኬቢ ይሰጣል

1. "የአምልኮ ዝማሬ" /ኪትል/
2. "የጥበብ ዝማሬ በዜማ የቀረበ" /ሞዊንክል/

ዴሪክ ኪድነር፣ *ቲንዳሌ ብኪ ሐተታ /ኮሜንተሪ/*፣ ቅጽ 15፣ ገጽ 195፣ ይሄንን ቃል ያገናኘዋል /ማለትም፣ ማስኪል/ ከጳውሎስ ጽሑፍ ጋር፣ 1 ቆሮ. 14፡15 ላይ ካለው። ይህ የሚያስደንቅ ነው፣ ግን የተጠናቀቀ አይደለም። እሱም ዘወትር እጅግ አስቸጋሪ ነው፣ የብኪ ጠቃሽ ዘይቤዎችን በአኪ ጽሑፎች ላይ ለማመልከት።

**47፡9** ይህ ቁጥር የሚያመለክተው፣ መሪዎች ሁሉ /ማለትም፣ የሕዝብ ወገናቸውን የሚወክሉ/ ወደ እስራኤል ተሰበሰቡ /ማለትም፣ የአብርሃም አምላክ ሕዝቦች፣ ዘፍ. 12:3፤ 22:18፤ ሮሜ 4፤ ገላ. 3:6-9)።

"ጋሻዎች" የሚለው ሐረግ ወታደራዊ ምስያ ነው፣ ለያህዌ ሁለንተናዊ ድል (መዝ. 46:8-11)።

ያህዌ በምድር ሁሉ ላይ መንገሡ በገዛ ራሱ ድርጊቶች ተፈጽሟል፣ /"እጅግ ከፍ ከፍ ብሏል" – ቢዲቢ 748፣ ኬቢ 828፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 46:10፤ ኢሳ. 2:11፣17፤ ደግሞም ዮሐንስ 3:14-15፣ ተመልከት፣ እዚያም "ከፍ ማለት" የሚለው ቃል "እጅግ ከፍ ማለት" የሚል ፍች የሚይዝበት/።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙር 45-50 በጋርዮሽ ምን አላቸው?
2. የመለኮትን መጠሪያዎች ዘርዝር፣ የእያንዳንዱንም ፍች አብራራ።
3. ቁጥር 9 ስለ ማን ነው የሚናገረው?
4. የመዝሙሩን ሁለንተናዊ ይዘቶች ዘርዝር። እነዚህስ ምንድነው አንድምታቸው?

# መዝሙር 48
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጽዮን ውበትና ክብር<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>የቆሬ ልጆች መዝሙር | የእግዚአብሔር ክብር በጽዮን | የጽዮንን ውበትና ደኅንነት ማክበሪያ መዝሙር | ጽዮን፣ የእግዚአብሔር ከተማ | ጽዮን የእግዚአብሔር ተራራ |
| 48:1-3 | 48:1-3 | 48:1-3 | 48:1-3 | 48:1-3 |
| 48:4-8 | 48:4-7 | 48:4-8 | 48:4-7 | 48:4-5 |
| | | | | 48:6-7 |
| | 48:8 | | 48:8 | 48:8 |
| 48:9-14 | 48:9-11 | 48:9-11 | 48:9-11 | 48:9-10ለ |
| | | | | 48:10ሐ-13ለ |
| | 48:12-14 | 48:12-14 | 48:12-14 | |
| | | | | 48:13ሐ-14 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር ስለዚአብሔር ልዩ ከተማና ሕዝብ ነው። እሱ ከእነርሱ ጋር ለእነርሱ ነው። ኢሳይያስ 26 ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት መ ተመልከት፣ በቀጥታ የዌብ ሳይት መስመር www.freebiblecommentary.org ለ"ከተማ" ምስያ።

ለ. ይህ መዝሙር ያመለክታልን፣ ኢየሩሳሌም የአዲሱ ዓለም አካላዊ ዋና ከተማ እንደምትሆን?
የዚህን መዝሙር ቃል በመጠቀም አንዱ ይህችን በታሪክ ውስጥ በተለያዩ ሕዝቦች የተያዘች፣ የተፈታች እና የተያዘች ኢየሩሳሌም እንዴት ሊገልጽ ይችላል?

ሐ. በዚህ ጉዳይ ላይ ታግያለሁ፣ ምክንያቱም እሱ የሚሊኒየም ንድፈ-ሐሳብ ዋና ነገር ስለሆነ። እባክዎትን ይመልከቱ የእኔን ማጠቃለያ፣ ልዩ ርዕስ ላይ፡ የብኪ የወደፊት ትንበያዎች በተቃርኖ የአኪ ትንበያዎች /ከእኔ የራዕይ ሐተታ /ኮሜንተሪ/ ላይ የተወሰደ/ መዝሙር 37 መግቢያ ላይ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 48፡1-3**

**[1]እግዚአብሔር ትልቅ ነው**
**በአምላካችን ከተማ በተቀደሰ ተራራ ምስጋናው ብዙ ነው።**
**[2]በሰሜን ወገን በመልካም ስፍራ የቆመ**
**የምድር ሁሉ ደስታ የጽዮን ተራራ ነው**
**እርሱም የትልቁ ንጉሥ ከተማ ነው።**
**[3]እግዚአብሔር በአዳራሾችዋ**
**መጠጊያ ሆኖ ይታወቃል።**

**48፡1-3** ኢየሩሳሌምና የተለያዩ ተራራዎቿ በተለያዩ መንገዶች እንዴት እንደተገለጹ ተገንዘብ።

1. የአምላካችን ከተማ፣ ቁ. 1
2. ቅዱሱ ተራራው፣ ቁ. 1
3. ያማረ ስፍራ (ቢዲቢ 832፣ እዚህጋ ብቻ፣ ብኪ ላይ፣ የማወዳደርያ ምልክት ይሆናል፣ እጅግ ያማረ)
4. የምድር ሁሉ ደስታ፣ ቁ. 2
5. የጽዮን ተራራ በሰሜን ጫፍ በኩል (ወይም "ሰሜን" = ዛፎን፣ የከነአናውያን አማልክት ተራራ፣ ከዑጋሬት በስተሰሜን፣ ኒዶቲ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 836)፣ ቁ. 2
6. የታላቁ ንጉሥ ከተማ፣ ቁ. 2
7. እግዚአብሔር በአዳራሾችዋ፣ መጠጊያ ሆኖ ይታወቃል፣ ቁ. 3

እነዚህ ገለጻዎች የሚጠቅሱት ሁለቱንም ነው፣ ሞሪያ ተራራ ላይ ያለው መቅደስ እና ሞላው የኢየሩሳሌም ከተማ፣ ዘወትር ጽዮን ተብሎ የሚጠራው።

**48፡1 "የአምላካችን ከተማ"** ይህ ሐረግ በርካታ ሐሳቦችን ሊጠቅስ ይችላል።

1. ከመልከ ጼዴቅ ጋር የምትያያዘውን ከተማ – ዘፍ. 14:18 (ማለትም፣ ሳሌም)
2. ያህዌ ስሙ እንዲኖርበት ያደረገው ከተማ – ዘዳ. 12:5፣11፣21፤ 14:23፣24፤ 16:2፣6፣11፤ 26:2
3. ዳዊት ከከነአናውያን የነጠቀው ከተማ (ማለትም፣ ጀቡስ)፣ ኋላ ላይም የእርሱ ከተማ የሆነ – 1 ሳሙ. 5:7፣9
4. የጌታ መልአክ መቅሠፍቱን ከከለከለበት ከተማ ጋር የተያያዘ፤ በዳዊት የተገዛ ስፍራ ለወደፊቱ ቤተ-መቅደስ የሚሆን – 2 ሳሙ. 24:15-17፣18-25፤ 2 ዜና. 3:1 (ማለትም፣ ሞሪያ ተራራ፣ የይስሐቅ መሠዊያ ስፍራ ሊሆን የሚችል፣ ዘፍ. 22:2)
5. ጽዮን እንደ ጀቡስ ተመሳሳይ – 2 ሳሙ. 5:7፤ 1 ዜና. 11:5 (ማለትም፣ ሞላውን የኢየሩሳሌም ከተማ መጥቀሻ መንገድ፣ ምንም እንኳ እርሷ በሰባት ኮረብቶች ላይ ብትሠራም፣ ጽዮን የተለመደ መጠሪያዋ ሆኗል

የመዝሙር 48 ችግር ቁጥር 2 ነው፣ "የጽዮን ተራራ በሩቅ ሰሜን።" እነዚህ ንድፈ-ሐሳብ ብቻ ናቸው።

1. እሱም ለሰማይ ዘይቤአዊ ነው፣ ያህዌ ለሚኖርበት – ኢሳ.14:13ሀ፣ለ፤ ራዕ. 3:12፤ 21:2፣10
2. እሱም እንደ ሌሎቹ መዝሙራት አንዳንድ የከነአን አፈ-ታሪክን ያካትታል (ማለትም፣ ዛፎን = ዕብራይስጥ "ሰሜን፣" ቢዲቢ 8) – ኢሳ. 14:13ሐ፣መ፤ሕዝ. 28:14

   እሱም የተለመደ ነበር በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ሃይማኖታዊ አስተሳሰብ፣ አማልክት በተራራ ጫፍ ይኖራሉ ብሎ ማሰብ (የጊልጋሚሽ አፈ-ታሪክ)። ይህም በተለይ እውነት ነው፣ ለዑጋሪቲክ በአል አፈታሪክ ግጥሞች፣ ከራስ ሻምራ። አማልክቱ ይገኙ ይኖሩ ነበር፣ በሰሜን ተራራ ሳፎን ወይም ዛፎን ተብሎ በሚጠራው። በአል እዚያ ዙፋን ነበረው፣ በአናዝ የተገነባ። የወንዱ አማልክት የፍንቂያውያን የመራባት አምልኮ *በአል ሳፎን* ይባል ነበር። ይህ ስም በፍንቂያውያን ቅኚዎች ተገኝቷል፣ በሜዲትራንያን አካባቢ። ይህ የሰሜን ተራራ ባህል፣ ከእስራኤል ቅዱስ ተራራ ከሞሪያ ጋር ፈጽሞ አይዛመድም (ዝከ. 20፡40)፣ የሁለቱም ምናባዊ ምንጭ ይመስላል፣ የኢሳ. 14:13-15 እና ሕዝ. 28:14፣16። ሮላንድ ዴ ቫዩክስ፣ የጥንት እስራኤል፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 279-281 ተመልከት።
3. አንዳንድ ሊቃውንት የዕብራይስጥ ተናባቢዎች የተለየ ምድብ ነው ይላሉ፣ "ተከተማይቱ በስተሰሜን በኩል"

"ከተማ" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ የያህዌ መገኛ የተለየ ስፍራ ማመልከቻ መንገድ ነው፣ እሱ በአኪ የቀጠለው።

1. ዕብ. 11፡10 — "እሱም (አብርሃም) ከተማ ይፈልግ ነበር፣ እግዚአብሔር የመሠረታት፣ የቀየሳት እና የገነባት"
2. ዕብ. 12፡22 — "ወደ ጽዮን ተራራ እና ወደ ሕያው አምላክ ከተማ መጥታችኋል፣ ወደ ሰማያዊቷ ኢየሩሳሌም"
3. ዕብ. 13፡14 — "እዚህ የሆነች ከተማ የለችንም፣ ነገር ግን የምትመጣውን ከተማ እንሻለን"
4. ራዕ. 3፡12 — "የአምላኬ ከተማ ስም፣ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም፣ እሷም ከሰማይ ከአምላኬ ዘንድ የምትወርደው"
5. ራዕ. 21፡2፣10 — "ከተማዋ፣ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም፣ ከሰማይ ከእግዚአብሔር ዘንድ ስትወርድ አየሁ"

**48፡2 "ተራራዎች"** ለጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ተራራዎች የአማልክት መኖርያ ነበሩ። በባቢሎን፣ እሱም ተፈጥሯዊ ተራራ የሌለው፣ ባለ ዕርከን ማማዎችን ይሠሩ ነበር (ማለትም፣ ባለ አራት ማዕዘን ትክል፣ ዘፍ. 11፡3-4) ሰማይና ምድር ለሚገናኙበት ስፍራ።

በእስራኤል ታሪክ በርካታ ጠቃሚ ተራራዎች አሉ።

1. ሲና ተራራ ያህዌ ከእስራኤል ጋር የተገናኘበትና ሕግን የሰጣት ስፍራ (ዘጸአት 19-20)
2. ጽዮን ተራራ፣ የዳዊት ከተማ (ሳሌም [ዘፍጥረት 14]፣ ኋላም ጀቡስ [2 ሳሙ. 5፡6-10])
3. ሞሪያ ተራራ፣ የመቅደሱ ስፍራ (ዘፍጥረት 22)
4. በዚህ መዝሙር ላይ ጽዮን ተራራ ከዛፎን ተራራ ይልቃል፣ የከነአናውያን አማልክት ተራራ (ከኦሎምፐስ ተራራ ጋር አቻ የሆነ፣ ለግሪክ አማልክት) ያህዌ ታላቅ ስለሆነ

*መዝሙር* ፡ **48፡4-8**

**4እነሆ፥ ነገሥታት ተከማችተው**
**በአንድነት መጥተዋል።**
**5እነርሱስ አይተው ተደነቁ፥**
**ደነገጡ፥ ታወኩ።**
**6መንቀጥቀጥ**
**እንደ ወላድ ምጥ በዚያ ያዛቸው።**
**7በኃይለኛ ነፋስ**
**የተርሴስን መርከቦች ትሰብራለህ።**
**8እንደ ሰማን እንዲሁ አየን**
**በሠራዊት ጌታ ከተማ፥ በአምላካችን ከተማ**
**እግዚአብሔር ለዘላለም ያጸናታል። ሴላህ**

**48፡4-8** ይህ አንጓ የሚያተኩረው የእግዚአብሔር ከተማ በምድር ላይ ያላትን ተጽዕኖ ነው (ዝኪ. ቁ. 2ሀ፤ 10ለ)። ምናባዊው ምስያ የሚገልጸው ፍርሃትና ማስጠንቀቂያ ነው፣ በእግዚአብሔር ኃይልና መገኘት ላይ በመመሥረት፣ በዚች የተለየች ዘላለማዊ ከተማ ላይ (ዝኪ. ቁ. 8ለ.ሐ)።

የአሕዛብ ነገሥታት ተጻራሪ እንደሆኑ፣ መዝሙር 2 ላይ፣ እዚህም እንደዚያው ነው። ርግጠኛ የሆነ ግጭት አለ፣ በቅዱስ ቃሉ ርዕዮተ ዓለም እና በአሕዛብ የጣዖት አምልኮ መካከል። ይህ የማይታይ፣ ግን ርግጥ የሆነ ግጭት የእያንዳንዱ ትውልድ እና የእያንዳንዱ ባህል ክፍል ነው። ግጭቱ የአህዳዊነት አካታች አለመሆን ነው።

**48፡6 "እንደ ወላድ ምጥ"** ይህ የተለመደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘይቤ ነው ለፍርሃት፣ ሥቃይ፣ ለድንገተኛ ጉዳት (ኢሳ. 13:8፤ 21:3፤ 26:17፤ ኤር. 4:31፤ ሆሴ. 13:13፤ ሚኪያስ 4:9፤ ዮሐንስ 16:21፤ ማርቆስ 13:8፤ 1 ተሰ. 5:3)።

**48፡7 "የምስራቅ ነፋስ"** ይህ ሙቅ የበረሀ ነፋስ ነው (ማለትም፣ የነፋስ ማዕበል፣ አሸዋ የሚያነሣ፣ ከዓረብኛ ቃል "ምስራቅ") እሱም ሰብልን የሚያደርቅ፣ አንበጣ የሚያመጣ፣ እናም የጥፋት ዘይቤ የሆነ (ኤር. 18:17፤ ሕዝ. 17:10፤ ሆሴ. 13:15፤ ዮናስ 4:8)።

▣ **"የተርሴስ መርከቦች"** የተርሴስ ርግጠኛ ስፍራ አልተለየም፣ ነገር ግን መልክዓ ምድራዊው አቀማመጥ ወደ ምዕራብ ራቅ ብሎ ሜዲትራኒያን ዳር ላይ ነው፣ እሱም የያህዌን ሁለንተናዊ ኃይል እንዲገልጽ ተመልክቷል። መርከቦቹ ትልልቆች፣ አስተማማኞች፣ በውቅያኖስ ላይ መጓዝ የሚችሉ ናቸው፣ በሜዲትራኒያን። እነርሱም የኃይልና የንግድ ተምሳሌት ናቸው።

**48፡8 "ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 3፡2 እና መግቢያ ለመዝሙር VII ላይ።

## መዝሙር ፡ 48፡9-14

**9 አምላክ ሆይ፥ በሕዝብህ መካከል**
**ምሕረትህን ተቀበልን።**
**10 አምላክ ሆይ፥ እንደ ስምህ**
**እንዲሁም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ**
**ምስጋናህ ነው ቀኝህ ጽድቅን የተሞላች ናት።**
**11 አቤቱ፥ ስለ ፍርድህ**
**የጽዮን ተራራ ደስ ይበለው፥**
**የአይሁድም ሴት ልጆች ሐሤት ያድርጉ።**
**12 ጽዮንን ከበቡአት፥ በዙሪያዋም ተመላለሱ፥**
**ግንቦችዋንም ቍጠሩ**
**13 በብርታትዋ ልባችሁን አኑሩ**
**አዳራሽዋን አስቡ**
**ለሚመጣው ትውልድ ትነግሩ ዘንድ።**
**14 ለዓለምና ለዘላለም**
**ይህ አምላካችን ነው፥**
**እርሱም ለዘላለም ይመራናል።**

**48፡9-14** ይህ አንጓ ያህዌን ያከብራል።

1. እነርሱ ስለ ቸርነቱ ሳያቋርጡ ያስቡ ዘንድ (ማለትም፣ የኪዳን ታማኝነት፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7 ላይ)
2. የእርሱ በመቅደስ በኢየሩሳሌም መገኘት
3. ስሙ (ባሕርዩ/ሥራው) እስከ ምድር ዳርቻ መመስገኑ
4. ቀኙ (ማለትም፣ ኃይል፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 7፡3-4) ጽድቅን መሞላቱ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡5 ላይ)
5. የይሁዳ ከተሞች (ማለትም፣ ሴቶች ልጆች) ከፍርዱ የተነሣ ይደሰታሉ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9፡5-6 ላይ)
6. ያማረ ከተማውን ተመልከቱ
7. እሱ ለዓለምና ለዘላለም ነው

**48፡11-13** ተከታታይ ትእዛዞች አሉ።

1. የጽዮን ተራራ ደስ ይበለው – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. የይሁዳ ሴቶች ልጆች ደስ ይበላቸው – ቢዲቢ 162፣ ኬቢ189፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. በጽዮን ተመላለሱ – ቢዲቢ 685፣ ኬቢ 738፣ *ቃል* ተተኳሪ
4. በዙሪያዋም ተራመዱ – ቢዲቢ 668፣ ኬቢ 722፣ *ሂፊል* ተተኳሪ
5. ግንቦችዋን ቁጠሩ – ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765፣ *ቃል* ተተኳሪ
6. በምሽጓ ልባችሁን አኑሩ – ቢዲቢ 1011፣ ኬቢ 1483፣ *ቃል* ተተኳሪ
7. በቤተ መንግሥቷ ተመላለሱ – ቢዲቢ 819፣ ኬቢ 946፣ *ፔል* ተተኳሪ

እነዚህ ድርጊቶችን የሚያመለክቱ ይሆናሉ (መዝ. 26፡6) (1) ኢያሱ ኢያሪኮን ሰባት ጊዜ ዙሪያውን ዞሯል፣ ኢያ. 6፡3-15 ወይም (2) ነህምያ ላይ የኢየሩሳሌም ግንቦች ምርቃት፣ ነህምያ 12።

▣ **"ግንቦች"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 153) የሚያመለክተው "የመጠበቂያ ማማ" ነው (2 ነገ. 9:17፤ 17:9፤ 18:8) እና ቀስተኞችን (2ዜና. 26:9፣10፣15፤ 32:5፤ ነህ. 3:25-27፤ ኢሳ. 2:15)።

◘ **"ምሽጎች"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 298) የሚጠቅሰው አንድም

1. የዙሪያውን ግድግዳ – ኢሳ. 26:1፤ ሰቆ. 2:8፤ ነሀ. 3:8
2. በሁለቱ የውጭ ግድግዳዎች መካከል ያለ ስፍራ – 2 ሳሙ. 20:15፤ ሰቆ. 2:8

◘ **"አዳራሾች" (ወይም "ምሽግ")** ይህ ቃል (ቢዲቢ 74) ሊያመለክት የሚችለው ማንኛውንም ዓይነት ትልቅ ሕንጻ ነው፣ በተመሸገ ከተማ (2 ነገ. 15:25፤ 2 ዜና. 36:19፤ ምሳ. 18:10፤ ኢሳ. 32:14፤ ኤር. 17:27፤ ሰቆ. 2:5፣7፤ ሆሴ. 8:14፤ አሞጽ 2:5፤ 6:8፤ ሚኪያስ 5:5)።

እነዚህ ሦስቱም ሁሉ ቃላት በወልነት የሚገልጹት ብርቱና የተመሸገ ከተማ ነው፣ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ። ነገር ግን የእርሷ ብርታትና ኗሪነት ያህዌ እዚያ በመኖሩ ምክንያት ነው!

**48:14**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"እስከ ሞት ድረስ"** |
| **አኪጀት** | **"*እስከ* ሞት እንኳ ቢሆን"** |
| **አየተመት** | **"ዘላለም"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ለዘላለም"** |
| **LXX** | **"ለዘመናት"** |
| **የተእመቅ** | **"እስከ ዘላለም"** |

"እስከ ሞት ድረስ" በሚለውና "ለዘላለም" በሚለው መካከል ያለው ልዩነት

1. የዕብራይስጡ ተናባቢ የቱጋ እንደሚከፋፈል ነው
2. የማሶረቲክ ሊቃውንት እጅግ ኋላ ላይ በዕብራይስጡ ጽሑፍ ላይ የጨመሯቸው አናባቢዎች

ሦስተኛ አማራጭ አለ ይሄንን የቅኔ ስንኝ ለመረዳት። አንድ ዓይነት የሆነ የዕብራይስጥ ቃል የዜማ ምትን ሊያመለክት ይችላል "እንደ አላሞዝ" (መዝሙር 46 ርዕስ)። እንደዚያ ከሆነ፣ እሱ ከመዝሙር 49 ጋር ይሄዳል። በዚህን ምክንያት ሊሆን ይችላል አኢመቅ ይሄንን ስንኝ የሚገድፈው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>*መመሪያ*</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር የሚያመለክተው ታሪካዊ ሁነትን ነው ወይስ የፍጻሜ ዘመንን?
2. ኢየሩሳሌም በአዲሱ ዘመን የያህዌ ዋና ከተማ ትሆናለችን?
3. ቁጥር 2 ለምን እጅግ አወዛጋቢ ሆነ? የመጽሐፍ ቅዱስ ደራስያን ከጣዖት አምላኪዎች ምንጮች ቃላትንና ምስያን ይጠቀማሉን?
4. ቁጥር 4-8 የሚገልጹት እንደ መዝሙር 2 ያለ ሁነት ነውን?
5. በዚህ መዝሙር ላይ ያሉትን ሁለንተናዊ ይዘቶች ዘርዝር?
6. ቁጥር 12-13 የሚገልጹት የአምልኮ ሥርዓት ሂደትን ነውን? እንደዚያ ከሆነ ይህንን የሚመስሉ ሌሎች ብኪ ላይ ይገኛሉን?

## መዝሙር 49
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| በህብት የመታመን ሞኝነት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ። የቆሬ ልጆች መዝሙር | የሰነፍ መተማመኛ | ጥሞና በሕይወትና ሀብት የአጭር ጊዜ መሆን | በሀብት የመታመን ስንፍና | የሀብት ከንቱነት |
| 49:1-4 | 49:1-4 | 49:1-4 | 49:1-4 | 49:1-2 |
| | | | | 49:3-4 |
| 49:5-9 | 49:5-9 | 49:5-9 | 49:5-9 | 49:5-6 |
| | | | | 49:7-8 |
| | | | | 49:9 |
| 49:10-12 | 49:10-12 | 49:10-12 | 49:10-12 | 49:10 |
| | | | | 49:11 |
| | | | | 49:12-13 |
| 49:13-15 | 49:13-15 | 49:13-15 | 49:13-15 | |
| | | | | 49:14ሀ-ሐ |
| | | | | 49:14መ-15 |
| 49:16-20 | 49:16-20 | 49:16-20 | 49:16-18 | 49:16-17 |
| | | | | 49:18-19 |
| | | | 49:19-20 | |
| | | | | 49:20 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙር 49 የጥበብ መዘሙር ነው (መዝሙር 37)። እሱም የተመለከተው ለኪዳን ማኅበረሰብ ነው፣ ለያህዌ ሳይሆን። እሱም እጅግ የበዛ የጋራ የሆነ ነገር አለው ከመጽሐፈ ምሳሌ ጋር፣ ከቀሪው መዝሙር ከሚመስለው ይልቅ። የቁጥር 3-4፣10-12፣13 ትይዩነትና ቃላት ተመልከት።

ለ. ፍሬ-ሐሳቡ ከመዝሙር 37 እና 73 ጋር ይመሳሰላል፣ እሱም በመሠረቱ እንደ "ሁለቱ መንገዶች" የሚገለጽ፤ ወደ ሕይወት የሚያመራው መንገድ እና ወደ ሞት የሚያመራው መንገድ (መዝሙር 1 እና ዘዳ. 30፡1፣15፣19)። ሁለቱ መንገዶች በተለይ ይታያሉ፣ ቁጥር 3 እና 5 ላይ፣ ከቁጥር 6 ጋር በመነጻጸር።

ሐ. ጭብጡ በሰውና በምድራዊ ሀብት የመታመንን ከንቱነት ነው። ይህ ያስገርም ይሆናል፣ ምክንያቱም ሀብት እና ስኬት ለኪዳን ታማኝነት የያህዌ ባርኮት ምልክት ተደርገው ይታዩ ስለነበር (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)።

### የቃልና የሐረግ ጥናት

## መዝሙር ፡ 49፡1-4

**1 አሕዛብ ሁላችሁ፥ ይህን ስሙ**
**በዓለም የምትኖሩትም ሁላችሁ፥ አድምጡ**
**2 ዝቅተኞችና ከፍተኞች፥**
**ባለጠጎችና ድሆች በአንድነት።**
**3 አፌ ጥበብን ይናገራል፥**
**የልቤም አሳብ ማስተዋልን።**
**4 ጆሮዬን ወደ ምሳሌ አዘነብላለሁ፥**
**በበገናም ምሥጢሬን እገልጣለሁ።**

**49፡1** ቁጥር 1 ሁለት ትይዩ ተተኳሪዎች አሉት (“ስሙ” [ቃል ተተኳሪ] እና “አድምጡ”[ሂፊል ተተኳሪ]። ጠቃሚ የሚሆነው የዚህ መዝሙር ደራሲ ያየው ሁለንተናዊ አንድምታ እንዳለው ነው፣ ከተስፋይቱ ምድር ዳርቻ ባለፈ (መዝ. 45፡16፤ 46፡10፤ 47፡1-2፣7-9፤ 48፡2፣10፤ 49፡1፤ 50፡1፣4፣12፣ ማለትም፣ “ሕዝቦች ሁሉ፣” “የዓለም ኗሪዎች ሁሉ”)። መታወስ ያለበት የጥበብ ሥነ ጽሑፍ (የመግቢያውን አንቀጽ ተመልከት፣ ገጽ xxv) ጽሑፋዊ ዘውግ ነው፣ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) እጅግ የታወቀ።

**49፡2 “ዝቅተኞችና ከፍተኞች”** ይህ በዕብራይስጥ እጅግ የተለመደ ዘይቤ ነው፣ ሁለት ጽንፎችንና በመካከሉ ያሉትን ማንኛውንም ነገር ለመግለጽ፣ (ትይዩውን ተመልከት “ሀብታም እና ደሀ”)። ይህ ሐረግ ራሱ እጅግ ያልተለመደ ነው፣ ምክንያቱም እርሱ ከጽሑፍ አኳያ “የሰው ልጆች” እና “የሰው ልጆች” በመሆኑ፣ ነገር ግን የሁለት የተለያዩ ቃላት መቀያየር ይሆናል፣ ለ“ሰው።” የመጀመሪያው አዳም የሚለው ቃል ነው (ቢዲቢ 9)፣ እሱም ዘወትር ፍችው “የሰው ልጅ።” ሁለተኛው ኢሽ የሚለው ቃል ነው (ቢዲቢ 35)፣ ለወንድ ሰው የወል ቃል። ደግሞም ሁለቱ ሐረጋት ተመሳሳይ ሊሆኑ ይችላሉ (አእመቅ፣ መዝ. 62፡9፤ ኢሳ. 2፡9፤ አእቅ መጽሐፍ ቅዱስ)።

**49፡3 “ጥበብ... ማስተዋል”** እነዚህ ሁለቱም ቃላት የብዙ ቁጥር ናቸው (የግርማው ብዙኀነት)፣ ይኸውም የማወዳደሪያ ሐሳብን የሚገልጽ። ይህ ከፍያለው ጥበብ ነው፣ የጠለቀውም ማስተዋል። ይህ የተመስጦ ጥበብ መምህር የእግዚአብሔርን እውነት ይናገራል።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመት** | **“ጥሞና”** |
| **አእቅ፣ የተእመቅ** | **“ሐሳብ”** |
| **አኢመቅ** | **“ለሆሳስ”** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **“ንግግር”** |
| **NAB** | **“ማነብነብ”** |

ይህ ብቸኛው የዚህ መልክ ሥር መከሰቻ ነው፣ הגה (ቢዲቢ 212)። የሥሩ መሠረታዊ ፍች “መጓጎር፣” “መሳግ፣” “ማነብነብ” ነው።

በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ እሱ የሚያመለክተው የመዝሙረኛውን ውስጠኛ ሐሳብ ነው። እሱ ሊሆን ይችላል

1. ጠቢብ/ፈላስፋ
2. ሌዋዊ/ዘማሪ
3. ካህን/ሥነ-መለኮታዊ

**49፡4 “ጆሮዬን ወደ ምሳሌ አዘነብላለሁ”** ይህ የሚነካ ዘይቤ ነው፣ ምሳሌን ሆን ብሎ የመስማት፣ ፍችውን መረዳት እንዲቻል። “ምሳሌ” የሚለው ቃል (ቢዲቢ 605) የጥንታዊ ጥበብ ቃል ነው፣ እሱም የእንቆቅልሽ፣ አዳጋች አባባሎች፣ ወይም የምሥጢራዊ እውነት ጽንሰ-ሐሳብ የያዘ የሚመስል። ሆኖም፣ የቁጥር 4 ሁለተኛው ስንኝ፣ እሱ እንቆቅልሽን እንደሚያቀርብ የማሳያ መንገድ ይመስላል (ቢዲቢ 295) ከዚያም በኋላ ፍችውን ይሰጣል። የቁጥር 4 ሁለቱ ግማሽ ክፍሎች መሠረታዊውን የጥበብ መልክ የሚያሳዩ ይመስላሉ። ደራሲው ይሄንን እውነት ያሳያል፣ የእርሱ ባህል/ዓለም ሰዎች ሊረዱ በሚችሉበት መንገድ።

## መዝሙር ፡ 49፡5-9

**5 ኃጢአት ተረከዜን በከበበኝ ጊዜ**
**በክፉ ቀን ለምን እፈራለሁ?**
**6 በኃይላቸው የሚታመኑ፥**
**በባለጠግነታቸውም ብዛት የሚመኩ**
**7 ወንድም ወንድሙን አያድንም፥**
**ሰውም አያድንም ቤዛውን ለእግዚአብሔር አይሰጥም፥**
**8-9 ለዘላለም እንዲኖር፥**
**ጥፋትንም እንዳያይ**
**የነፍሳቸው ለውጥ ከብሮአልና፥**
**ለዘላለምም ቀርቶአልና።**

**49፡5-9 “በክፉ ቀን ለምን እፈራለሁ”** ይህ በዚህ መዝሙር ላይ እየዳበረ የሚሄድ ጭብጥ ነው።

1. ሕይወት – ኢዮብ 11፡17፤ መዝ. 39፡5፤ 89፡47
2. ዓለም – መዝ. 17፡14

ፍች የሚወሰነው በዐውደ-ጽሑፍ መሆኑን አስታውስ፣ በመዝገበ-ቃላት/ሥርወ-ቃላት ሳይሆን።

መልካም ሰዎች ዘወትር ይደነቃሉ፣ ስለ ሕይወት ፍትሐዊነት (ኢዮብ፣ መዝሙር 73፤ ዕንባቆም)። ክፉዎች ዘወትር ይበለጽጋሉ፣ ጻድቃንም መከራ ይቀበላሉ። ይኸም ሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30ን የሚቃረን ይመስላል። ያህዌ የእሱን ሕዝብ በረከትና ብልጽግና አሕዛብን ወደ ራሱ ለመማረክ መጠቀምን ፈልጓል። ሆኖም፣ በዘፍጥረት 3 ውድቀት ሳቢያ፣ የኪዳኑ የሰው ልጅ እንኳ ቢሆን ሕጉን መጠበቅ አልቻለም። ብቸኛው ብልጽግና የመጣው ወደ ግፈኛ፣ ስግብግብ፣ ኃይለኛ ሕዝብ ነው።

ይህ ዓለም እግዚአብሔር እንዲሆን የፈጠረው አይደለም። የእርሱ ሕዝብ የእርሱን ባሕርይ ማሳየት አልቻለም (ሕዝ. 36፡22-23)። የወደቁት የሰው ልጆች ራሳቸውን ወይም ቤተሰባቸውን፣ ወይም ጎረቤቶቻቸውን ማዳን/መዋጀት አይችሉም!

**49፡5 "የጠላቶቼ ኃጢአት ከበበኝ"** ኪጀት "ተረከዝ" የሚል ቃል አለው በ"ጠላቶች" ምትክ። የመነሻው ዕብራይስጥ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 784) ከያዕቆብ ጋር ይያያዛል፣ በሚወለድበት ጊዜ የወንድሙን ተረከዝ እንደያዘ፣ እና ስለዚህ፣ "አጭበርባሪ፣" "ነጣቂ፣" ወይም "ቀሚ፣" በሚል ተሰየመ። ይህ "ጠላት" የሚለው ቃል ጽንሰ-ሐሳብ ነው፣ እዚህ።

**49፡6 "በባለጠግነታቸውም ብዛት የሚመኩ"** ይህ ግሥ "መመካት" (ቢ.ዲ.ቢ. 105፣ ኬቢ. 120) ባብዛኛው የሚከሰተው መዝሙር እና ኢሳይያስ ላይ ነው (ኢሳ. 26:3-4፤ 30:15)። መዝሙር 37 ላይ በእግዚአብሔር ብቻ እንድንታመን ተምረናል! ይህ ቁጥር ቀጥተኛ ተቃራኒው ነው፣ ሰዎች በራሳቸው ሲታመኑ ወይም በቁሳዊ ሀብታቸው (ኢዮብ 31:24፤ መዝ. 62:10፤ ምሳ. 11:28፤ 23:4-5፤ ማርቆስ 10:23-31፤ 1 ጢሞ. 6:17-19)።

**49:7 "ወንድም ወንድሙን አያድንም"** በዕብራይስጥ "ወንድም" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 26) በቅድሚያ ለግነት ነው የሚከሰተው። አእመቅ፣ የተእመቅ፣ RSV፣ አየተመት אח (ወንድም)ን ወደ אך (በርግጥ ይለውጣሉ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 36)። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 245) ለ "ወንድም" "ሀ" ደረጃ ይሰጣል። ዕብራይስጡ የሚያስቀምጠው ሰው ራሱን/ራሷን እንኳ እንደማያድን ነው (ማለትም፣ ማዳን፣ መታደግ)።

**49:7፤8 "መዋጀት... መቤዠት... መዋጀት"** ሁለት የዕብራይስጥ ግሦች አሉ፡

1. "መዋጀት" – ቢ.ዲ.ቢ. 804፣ ኬቢ. 911፣ *ቃል* ያልተወሰነ የተጠናቀቀ እና ያልተጠናቀቀ ግሥ፣ የተመሳሳይ ሥር፣ ለአጽንዖት
2. "መቤዠት" (ቢ.ዲ.ቢ. 145 I ያይደለ) – ቢ.ዲ.ቢ. 678፣ ኬቢ. 733፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ ከቢ.ዲ.ቢ. 497 I ጋር፣ "ሰው የሕይወቱን ዋጋ ለእግዚአብሔር ሊሰጥ አይችልም"

ሁለቱም የሚያመለክቱት አንዱን መልሶ መግዛትን ነው፣ ከባርነት ወይም በጦር እስረኝነት ከመያዝ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መቤዠት/መዋጀት መዝ. 19:14 ላይ።

**49:8-9 "የነፍሳቸው ለውጥ ከብሮአልና፥**

**ለዘላለምም ቀርቶአልና።"** ይህ ቅንፋዊ አስተሳሰብ ነው፣ እሱም አጽንዖት የሚሰጠው የቱንም ያህል ሰው ሀብታም ቢሆን፣ ሕይወትን ለማራዘም የሚደረግ ክፍያ ወይም ከሞት ወዲያ ሕይወትን ለማስጠበቅ እጅግ ከፍ ያለ ነው። እዚህጋ ነው የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል የምስራች የሚሆነው (ኢሳይያስ 53፤ ማርቆስ 10:45፤ 2 ቆሮ. 5:21)!

ትይዩውን ተገንዘብ።

1. ለዘላለም ቀርቷልና (ቢ.ዲ.ቢ. 761) – ቢ.ዲ.ቢ. 292፣ ኬቢ. 292፣ *ቃል* የተጠናቀቀ ከዋው ጋር
2. ለዘላለም መኖር ይኖርበታል (ቢ.ዲ.ቢ. 664) – ቢ.ዲ.ቢ. 310፣ ኬቢ. 309፣ *ቃል* ተጓዳኝ
3. ጥልቁን መመልከት አይኖርበትም (ቢ.ዲ.ቢ. 1001) – ቢ.ዲ.ቢ. 906፣ ኬቢ. 1157፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ

ክርስቲያኖች ይህንን ዓይነት የመሳሰሉ ጽሑፎችን ለመተርጎም ይቸገራሉ፣ ምክንያቱም የእኛን የአኪ የቃላት መረዳቶችና ፍችዎች በእነዚህ የብኪ ጽንሰ-ሐሳቦች ላይ በማንበባችን ነው። ይህ በዋነኛነት ከኢሳይያስ 53 ወይም ከዮሐንስ 3፡16 ጋር አይዛመድም። ይህ የሚናገረው ረጅም፣ ጤናማ፣ የብልጽግና ሕይወት ጋር ነው። ብልጽግና ይሄንን ሊያረጋግጥ አይችልም! በወደቀው ዓለም የኪዳን ታዛዥነት እንኳ ይሄንን ሊያረጋገጥ አይችልም (ማለትም፣ ኢዮብ፣ ይስሐቅ፣ እስራኤል)።

በርግጥ አንዳንድ ፍንጮች አሉ፣ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት፣ ብኪ ላይ (ማለትም፣ ኢዮብ 14:14-15፤ 19:25-27፤መዝ. 16:10፤ ዳን. 12:2)፣ ነገር ግን ባብዛኛው ክፍል ብኪ የሚገልጸው ይህንን ሕይወት ነው!

**49፡8 "የከበረ"** በብኪ ዐውደ-ጽሑፍ ላይ፣ የመዋጀት/መቤዠት ዋጋ የነበረው

1. ንጹሕ የሆነ እንስሳ ሞት፣ እንደ ተቀያሪ (ሌዋውያን 4) ለኃጢአተኛ የሰው ልጅ ነፍስ ወይም ሌዋውያን 16 ለእምነት ማኅበረሰብ
2. መዝሙር 51 ላይ ምንም ዓይነት መሥዋዕት አልነበረም፣ ሆን ብሎ ለሠራው ለዳዊት ኃጢአት (ሌዋ. 4:2፣22፣27፤ 5:15-18፤ 22:14)፣ ስለዚህ ዳዊት "የተሰበረ እና ያዘነ ልብ" አቀረበ (መዝ. 51:17)
3. አጠቃላይ ዋጋው የተከፈለው በ "እግዚአብሔር በግ እርሱም የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ" ነው (ዮሐንስ 1፡29)። ይህም ተተንብዮአል ኢሳ. 52:13-53:12 (ማለትም፣ መከራ የሚቀበለው አገልጋይ)። ይህ የተቀያሪ መዋጃ ጽንሰ-ሐሳብ በኢየሱስ ተገልጿል (ማርቆስ 10:45)፣ ጳውሎስ (ገላ. 1:4፤ 1 ቆሮ. 15:3፤ 2ቆሮ. 5:21)፣ ጴጥሮስ (1 ጴጥ. 2:21-24)፣ እና የዕብራውያን ጸሐፊ (ዕብ. 7:26-27፤ 9:28)።

**49፡9 "ለዘላለም እንዲኖር፥**

**ጥፋትንም እንዳያይ"** እዚህጋ የብልጽግና ችግር አለ። እሱም የመዳረሻውን ምላሽ አይሰጥም። እሱም ሰውን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሊያደርግ አይችልም፣ እናም ሕይወትን ሊያራዝም አይችልም። ስለዚህ፣ እሱ የሐሰት ተስፋ ነው፤ እሱ ወዲያው ታይቶ የሚጠፋ ብልጭታ ነው። ብቸኛው እውነተኛ ብርሃን፣ ብቸኛው እውነተኛ ተስፋ፣ እና ብቸኛው እውነተኛ ሕይወት በእግዚአብሔር ነው የሚገኘው።

**መዝሙር ፡ 49፡10-12**

**[10]ብልሃተኞች እንዲሞቱ፥**
**ሰነፎችና ደንቆሮች በአንድነት እንዲጠፉ፥**

**ገንዘባቸውንም ለሌሎች እንዲተዉ አይቶአል።**
**[11]በልባቸውም ቤታቸው ለዘላለም የሚኖር፥**
**ማደሪያቸውም ለልጆች ልጅ የሚሆን ይመስላቸዋል**
**በየአገራቸውም ስማቸው ይጠራል።**
**[12]ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም**
**እንደሚጠፉ እንስሶች መሰለ።**

**49:10 "ብልሃተኞች እንዲሞቱ አይቷልና**
**ሰነፎችችና ደንቆሮች በአንድነት እንዲጠፉ፥** ምንም እንኳ ይህ ዘይቤ መክ. 2:15፣16 ላይ ከሚገኘው ጋር ተመሳሳይ ቢሆንም፣ እዚህጋ በሌላ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። እዚህ፣ የሁሉም ነገሮች ሞት፣ ሰዎችንና እንሰሳትን ጨምሮ፣ የሚዛመደው በሀብታቸው ረጅም ዕድሜ መግዛት ካለመቻላቸው ጋር ነው። ሦስት የተለያዩ ሰዎች ወይም ወገኖች ቁ. 10 ላይ የተካተቱ ይመስላል፤ ጠቢብ ሰው፣ ደደብ ሰው፣ ስሜት-አልባ ሰው። እንሰሳት ቁ. 12 እና 20 ላይ ከመጠቀሳቸው የተነሣ አንዳንዶች የሚመለከቷቸው፣ እዚህ የሚጠቅሱት "ስሜተ ቢስ" ነው (ቢዲቢ 129፣ እንሰሳ ዓይነት፣ መዝ. 73:22)።

▣ **"ገንዘባቸውንም ለሌሎች እንዲተዉ"** እንደገና መክ. 2:18-23 እጅግ የሚረዳ ነው። ምንም ያህል አንድ ሰው ሀብታም ቢሆንም፣ እርሱ/እርሷ ሲሞቱ፣ ሁሉንም ለሌላ ነው የሚተዉት።

**49:11 "በልባቸውም ቤታቸው ለዘላለም የሚኖር፥"** የኤምቲ ዕብራይስጥ ጽሑፍ፣ ሀብታም ሰው እርሱም ሆነ ሀብቱ ለዘላለም እንደሚኖሩ ያምናል የሚል ሐሳብ ይዟል። ሆኖም፣ LXX ሐሳቡን ይቀይረዋል፣ "መቃብራቸው የዘላለም ቤታቸው ነው" ወደሚል። የትኛውም እውነት ቢሆን፣ እሱ አሁንም የሚያሳየው በሀብት የመታመንን የመዳረሻ ሞኝነት ነው።
ዩቢኤስ ጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 246) አለው
1. קִרְבָּם – የውስጣቸው (አአመመቅ፣ "ውስጣዊ ሐሳብ፣" ቢዲቢ 899)
2. קִבְרָם – መቃብራቸው (ቢዲቢ 868)። እሱም "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ) ለአማራጭ ቁ. 2 (አኪመቅ፣ የተእመቅ፣ ጀፒኤስኦኤ፣ LXX፣ ሶርያ፣ ቫልጌት)
"ቤቶች" የሚለው ቃል ሊያመለክት የሚችለው የተለሰኑ ያሸበረቁ እና ውድ መቃብሮችን ነው። እነዚህ፣ እንደ ፈርዖን የሚያስቡት ሥጋዊ ሐውልቶች በራሳቸው መታሰቢያቸውን ያረጋግጣሉ፣ እናም ሙት አለመሆናቸውን በሚል መልኩ።

▣ **"በየአገራቸውም ስማቸው ይጠራል።"** ሰዎች እንዲታሰቡ ለማረጋገጥ ከሚሞክሩባቸው መንገዶች አንደኛው መልክዓ ምድራዊ ስፍራዎችን በእነርሱ አስከትለው መሰየም ነው (ወይም ሕጋዊ ድርጊቶችን በስማቸው ማድረግ)። ይኼም ደግሞ ሞኝነት ነው፣ ስሞች ከዘመን ዘመን ስለሚቀያየሩ።

**49:12 "ሰው ግን ክቡር ሆኖ ሳለ አያውቅም"** ተመሳሳይ ትይዩ ለመስጠት ከመሞከር አኳያ ቁጥር 12 እና 20 ላይ አእመቅ እና የተእመቅ ይለውጡታል –
"በክብር" (አአመመቅ፣ "ባሸበረቀ")፣ בִּיקָר ፣ ቢዲቢ 430፣ የሚለውን ወደ
"ክብት" (አእመቅ፣ የተእመቅ፣ "ምድጃ")፣ בָּקָר ፣ ቢዲቢ 133
ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት "በክብር" ለሚለው "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ) ቁጥር 12 ላይ "ሀ" ደረጃ (ርግጠኛ) ቁጥር 20 ላይ። ግልጽ የሆነው፣ በሀብት መመካትና መታበይ እዚህጋ አጽንዖት እንደተሰጠው ነው (መክ. 3:19-23)።

## መዝሙር ፡ 49:13-15

**[13]ይህች መንገዳቸው መሰናክላቸው ናት፥**
**ከእነርሱም በኋላ የሚመጡ በአፋቸው እሺ ይላሉ። ሴላህ**
**[14]እንደ በጎች ወደ ሲኦል የሚሄዱ ናቸው፥**
**እረኛቸውም ሞት ነው**
**ቅኖችንም በማለዳ ይገዙአቸዋል፥**
**ውበታቸውም ከመኖሪያቸው ተለይታ**
**በሲኦል ታረጃለች።**
**[15]ነገር ግን እግዚአብሔር ይቀበለኛልና**
**ነፍሴን ከሲኦል እጅ ይቤዣታል። ሴላህ**

**49:13 "ይህ የሰነፎች መንገዳቸው ነውና"** ሰነፍ የሚጠቅሰው አንድም (1) እግዚአብሔርን እንደሚያውቅ የሚናገር ሰው፣ ነገር ግን አኗኗሩ እግዚአብሔር የለም የሆነ ወይም (2) በግልጽ ክፉ የሆነ ሰው። በብኪ እንደ ኢ-አማኒ ያለ በርግጠኝነት እንዲህ ያለ ነገር የለም (ኢሳ. 53:1)።
"መንገድ" የብኪ ፈሊጥ ነው ለሕይወት ስልት። ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 1:1 ላይ።

▣ **"ከእነርሱም በኋላ የሚመጡ በአፋቸው እሺ ይላሉ።"** ይህ የሚያመለክተው የትዕቢት ሀብት ተጽዕኖ በሕይወት ፍልስፍናቸው ላይ ያለውን ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:1 ላይ። እሱም ልጆቻቸውን፣ ተማሪዎቻቸውን፣ ሌሎች ሀብታም ለመሆን የሚሹ ሰዎች፣ ወይም ባልንጀሮቻቸውን የሚያመለክት ነው። ይህ የፍጻሜ ውጤት ነው፣ የሐሰተኛ ርዕዮተ-ዓለም (ማቴ. 15:14፤ ሉቃስ 6:23)።

◘ **"ሴላህ"** ይህ ብዙ ውይይት የተካሄደበት ቃል ነው፣ ነገር ግን አነስተኛ ስምምነት የተደረሰበት። አንዳንዶች የሚሉት እሱ የሚያመለክተው

1. ቆምታ
2. የድምጽ መነሣት
3. የዜማ ጣልቃ
4. ለዘላለም፣ እንደ ራቢዎች

የበርካታ ትርጉሞች መኖር የሚያሳየው ሐቅ፣ ማንም በርግጠኝነት እንደማያውቀው ነው። ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 3፡2 እና መግቢያ ለመዝሙር፣ VII.

**40፡14 "እንደ በጎች ወደ ሲኦል የሚሄዱ ናቸው"** ሲኦል የሚለው ቃል የሚያመለክተው "የሙታን ስፍራ" ነው፣ በብኪ። እሱም ንቁ እንደሚኮንበት ስፍራ ይታያል፣ ነገር ግን ደስታ አይኖርም፣ ኅብረት አይኖርም፣ እናም የጨፈገገ እይታ ያለበት ጨለማ ነው፣ የጸጥታ ቀናት። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡6 ላይ።

◘ **"እረኛቸው ሞት ነው"** ይህ በጥሬው "ሞት ይመግባቸዋል" ነው። እንዴት ያለው አስፈሪ ትይዩ ነው፣ ከመዝ. 23፡1 ውበት ጋር። ሞት በዚህ ዓለም ደስታ እነርሱን ያጠምዳቸዋል፣ በመጨረሻ ግን መርዝ ይሆናል (ምሳሌ 1-8)።

◘ **"ቅኖችንም በማለዳ ይገዙአቸዋል፥"** ይህ እውነት በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ ላይ ተስተምሯል (ዳን. 7፡18፤ ሚል. 4፡3፤ 1 ቆሮ. 6፡2፤ራዕ. 2፡26)።

◘ **"በማለዳ"** ይህ ሊያመለክት የሚችለው

1. የእግዚአብሔር እውነት ብርሃን
2. የሕይወት ብርሃን
3. የፍጻሜ ዘመን ማለዳ ወይም የአዲስ ቀን ብስራት

ኒዶቴ ቅጽ 1፣ ገጽ 327፣ በ "ብርሃን" የሚወከሉ መልካም ነገሮች ዝርዝር አለው።

1. ደኅንነት – መዝ. 27፡1፤ ኢሳ. 49፡6
2. ብልጽግና እና ሰላም – ኢሳ. 45፡7
3. የያህዌ ኪዳን – ኢሳ. 42፡6
4. ፍትሕ እና ጽድቅ – ኢሳ. 51፡4፤ 59፡9
5. ባርኮት – መዝ. 89፡15
6. እግዚአብሔር ራሱ – መዝ. 27፡1፤ ኢሳ. 60፡1-3፣19-20
7. መከራ የሚቀበል አገልጋይ – ኢሳ. 42፡6፤ 49፡6
8. መሲሕ – ኢሳ. 9፡2

የዕብራይስጥን ተናባቢዎች በተለያየ መንገድ መከፋፈል ይቻላል፣ "በቀጥታ ወደ መቃብር ይሄዳሉ" (ኒዶቴ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 713)። ይኽም ከአንጓው ማዕከላዊ እውነት ጋር በተሻለ ይገጥማል (አየተመት፣ የተእመቅ)።

◘ "መጨረስ" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 115፣ ኬቢ 132፣ ፔል ያልተወሰነ አወቃቀር) በጥሬው "ማርጀት" ማለት ነው። ስለዚህ የስንኙ ሐሳብ

1. ሲኦል ይበላቸዋል (የሲኦል ዘይቤ፣ እንደ ተራብ እንስሳ ወይም ለከነአናውያን የሞት አምላክ ጠቃሽ፣ *ምት*፤ አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ተመልከት፣ ገጽ 785፣ የግርጌ ማስታወሻና ኤቢ፣ ገጽ 300)።
2. አካል በአቧራ ላይ ይበሰብሳል፣ ሁሉም አካላት ከሞት በኋላ እንደሚሆኑት (አየተመት፣ አእት፣ ጀፒኤስኦኤ)።

**49፡15 "ጌታ ግን ነፍሴን ከሲኦል ኃይል ይቤጃታል፤**
**እርሱም ይቀበለኛልና"** እንዴት ያለው ብርቱ እውነት ነው! የግል ይዞቱን ተገንዘብ — "እኔ"! እዚህጋ ለከሕይወት በኋላ የመጀመሪያው ማረጋገጫ አለን (ወይም ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ወዳጅነት፣ እዚህ እና አሁን በሕይወት ዘመን ሁሉ እና መተማመኛው ቀጣይነት ያለው!)፣ የተመሠረተውም በሰው ሥራ ላይ አይደለም፣ ግን በእግዚአብሔር ፍቅር ላይ እንጂ። እዚህ፣ ግላዊ እምነት፣ ብሎም የመታዘዝ ሕይወትና መታመን፣ ከአምላካችን ጋር ዘላለም የመሆን ሽልማት ያገኛሉ (ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 23፡6 ላይ)።

"መቀበል" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 542፣ ኬቢ 534) ዘፍ. 5፡24 ላይ ለሔኖክ ጥቅም ላይ ውሏል። እሱ ወደ ያህዌ መገኛ ተሸጋገረ!

ለሲኦል መዝ. 6፡5 እና 9፡13 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

## መዝሙር ፡ 49፡16-20

**16 የሰው ባለጠግነት**
**የቤቱም ክብር በበዛ ጊዜ አትፍራ፥**
**17 በሞተ ጊዜ ከእርሱ ጋር ምንም አይወስድምና፥**
**ክብሩም ከእርሱ በኋላ አይወርድምና።**
**18 በሕይወቱ ሳለ ነፍሱን ባርኮአልና**
**ለሰውነቱ መልካም ብታደርግለት ያመሰግንሃል።**
**19 ሆኖም ወደ አባቶቹ ትውልድ ይወርዳል**
**ለዘላለም ብርሃንን አያይም።**
**20 አእምሮ የሌለው ክቡር ሰው**
**እንደሚጠፋ እንስሶች መሰለ።**

**49:17 "በሞተ ጊዜ ከእርሱ ጋር ምንም አይወስድምና"** ይህ እውነት ነው በሀብት የሚታመኑ በሞት ጊዜ ጥለውት እንደሚሄዱ (1 ጢሞ. 6:7)። ራዕይ 13:14 የሚነግረን ለእግዚአብሔር የኖሩትን መልካም ሥራ እንደሚከተላቸው ነው። የሕይወት መጽሐፍ እና የድርጊት መጽሐፍ አለ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9:5 ላይ)። እግዚአብሔር ይሸልማቸዋል የሚወዱትንና የሚያገለግሉትን። የፍርድ ቀን ይመጣል — አምላካችንን ለሚያውቁት የሽልማት ቀን ይሆንላቸዋል፣ ነገር ግን በራሳቸው ለሚታመኑ፣ የዘላለም መለየት ቀን ይሆንባቸዋል (ማቴ. 25:31-46፤ ራዕ. 20:11-15)።

▣ **"ክብሩ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል (ቢዲቢ 458 II) ፍቺው የሚሆነው

1. በረከት (መትረፍረፍ)
2. አክብሮት
3. ክብር

▣ ***"መውረድ"*** ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ 432፣ ኬቢ 434፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) የሚገልጸው ሙታን በመሬት ውስጥ ወይም በምድር ውስጥ ናቸው የሚለውን እምነት ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው? መዝ. 1:6። ይህም ወደ ሙታን አገር መውረድን መግለጫ መንገድ ነው። የብኪ ሴማውያን ሙታናቸውን ይቀብራሉ።

**49:18 "በሕይወቱ ሳለ ነፍሱን ባርኮአልና"** ይህ ቁጥር በግልጽ የሚዘመደው በትዕቢተኝነት የሚመኩትን ነው፣ በገዛ ራሳቸው ሀብት በመታመን። ነገር ግን ቁልምጫ ምትሐታዊ ነው። የእግዚአብሔር ዓለም ሞራላዊ ነው፣ እናም እያንዳንዱ ለእግዚአብሔር ምላሽ ሊሰጥ ይገባል (ዳን. 12:2፤ ማቴ. 25:31-46፤ 2 ቆሮ. 5:8፤ ራዕ. 20:11-15)።

ለ "እርሱ" (*ኔፌሽ*) መዝ. 3:2 ማስታወሻ ተመልከት።

**49:19 "ሆኖም ወደ አባቶቹ ትውልድ ይወርዳል"** ይህ የሚያመለክተው ሐቅ የብኪ ቀብር ዘወትር የሚደረገው በቤተ-ሰብ መቃብር፣ በዋሻዎች መሆኑን ነው። ይህ የብኪ ጠቃሽ ነው፣ ከቤተሰብ ጋር ስለ መቀበር።

▣ ***"ብርሃንን ፈጽሞ አያዩም"*** ይህ ተመሳሳይ ጽንሰ-ሐሳብን የሚጠቅስ ይመስላል ቁ. 14 ላይ እንዳለው። እሱም የሕይወት ብርሃን፣ የእውነት ብርሃን ማለት ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን የሚሆነው የሲኦል ጨለማ ነው — አምላካችንን የማያውቁት የሚኖሩበት ስፍራ (ኢዮብ 3:16፤ 33:28፣ 30፤ መዝ. 36:9)።

**49:20** ይህ በትክክል እንደ ቁጥር 12 ያለ ነው፣ እናም ከዚህ መዝሙር ማጠቃለያ ጋር ይገጥማል። እሱ የሚያሳዝን ነው ነገር ግን የጠፊው ሰው እውነተኛ ስዕል፣ በገዛ ራሱ ሀብት ተጠቅሎ እንደቆመ (ማቴ. 7:13-14)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታስላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የአይሁድ ጥበብ ለሞላው ዓለም ለመናገር ለምን ይፈልጋል?
2. በክፉው ቀን ላለመፍራት መዝሙረኛው ምን ምክንያቶች ነው የሚያቀርበው?
3. "መዋጀት" የሚለውን ቃል አብራራ።
4. ይህ መዝሙር ከመክብብ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
5. ሲኦል ምንድነው?
6. የቁጥር 15 ሥነ-መለኮታዊ አንድምታ ምንድነው?

# መዝሙር 50
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር የጻድቁና የኃጢአተኛው ፈራጅ <u>ኤምቲ መግቢያ</u> የአሳፍ መዝሙር | እግዚአብሔር ጻድቅ ፈራጅ | የመለኮታዊ ፍርድ የአምልኮ ሥርዓት | እውነተኛ አምልኮ | በመንፈስና በእውነት ማምለክ |
| 50:1-6 | 50:1-3 | 50:1-2 | 50:1-2 | 50:1-3ሀ |
| | | 50:3-6 | 50:3-6 | 50:3ለ-4 |
| | 50:4-6 | | | |
| | | | | 50:5-6 |
| 50:7-15 | 50:7-11 | 50:7-11 | 50:7-11 | 50:7 |
| | | | | 50:8-9 |
| | | | | 50:10-11 |
| | 50:12-15 | 50:12-15 | 50:12-15 | 50:12-13 |
| | | | | 50:14-16ሀ |
| 50:16-21 | 50:16-21 | 50:16-18 | 50:16-18 | 50:16ለ-17 |
| | | | | 50:18-19 |
| | | 50:19-21 | 50:19-21 | |
| | | | | 50:20-21 |
| 50:22-23 | 50:22-23 | 50:22-23 | 50:22-23 | 50:22-23 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ ሌለኛው መዝሙር ነው እሱም ሁለንተናዊ ነገሮችን የያዘ (ዝከ. 50:1፣4፣12፤ መዝ. 45:16፤ 46:10፤ 47:2፤ 48:2፣10፤ 49:1)። ይህ ሌለኛው መንገድ ነው፣ ያህዌን እንደ ፈጣሪ ለማጽናት (መዝሙር 104)፣ ብቸኛው አምላክ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት መዝ. 2፡ 7 ላይ)።

ለ. እሱ ፈጣሪ ከመሆኑ የተነሣ፣ እሱ ብቸኛ ፈራጅ ነው። ሰዎች ይፈረድባቸዋል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ግንኙነት፣

1. እምነት
2. መታዘዝ
3. አምልኮ

የአምልኮ ሥርዓትን ወይም የአንድነት አምልኮ አገባቦችን መፈጸም ሳይሆን። እውነተኛ እምነት የልብ ነው፣ ከእጅ በፊት!

ሐ. ይህ መዝሙር ስለ ሰዎች ሁሉ ፍርድ አይደለም፣ ግን ስለ ኪዳኑ ሕዝብ ፍርድ ነው፣ ሰማይ፣ መሬት፣ እና ሰዎች ሁሉ እንደሚመለከቱት። ይሄም ፍርድ ዓላማው

1. አንዳንድ የዛለ የእምነት ልብን ለመመለስ
2. የአንዳንዶችን የተሳሳተ እምነት ለመግለጥ

መ. ይህ መዝሙር የሚገልጸው
1. የአምልኮ ሥርዓት-ተኮር ተከታዮችን (ዝከ. ቁ. 7-15)
2. እምነት የሌላቸው ተከታዮችን (ዝከ. ቁ. 16-21)
3. አጭር ማጠቃለያ ቁ. 22-23 ላይ

ሐ. በርካታ ጠቃሾች አሉ፣ የንግግር። ተገንዘቡ
1. የንግግር፣ ቁ. 1ሀ
2-3 ስብከት (ማለትም፣ ለመመስከር ወይም ለማረጋገጥ)፣ ቁ. 1ለ፣ 4
4. ዝም ያለማለት፣ ቁ. 3፣ 21ሀ
5-6 የያህዌ ቀጥተኛ ንግግር፣ ቁ. 5፣7
7. ማወጅ፣ ቁ. 6ሀ
8. እናገራለሁ፣ ቁ. 7ሀ
9. እመሰክራለሁ፣ ቁ. 7ኀ
10. አረጋግጣለሁ፣ ቁ. 8፣21
11. የምስጋና መሥዋዕት ቁ. 14ሀ፣ 23ሀ
12. ያህዌ ይላል፣ ቁ. 16ሀ (አብዛኛው መዝሙር ያህዌ ሲናገር ነው፣ ቁ. 5፣ 7-15፣ 16-21፣ 22-23)
13. ይናገራል፣ ቁ. 16ለ
14. ቃሌ፣ ቁ. 17ለ
15. አፍህ፣ ቁ. 19ሀ
16. አንደበትህ፣ ቁ. 19ለ
17. ይናገራል፣ ቁ. 20ሀ
18. ስም አጥፊ ቃላት፣ ቁ. 20ለ
በንግግራቸው ታውቋቸዋላችሁ፣ ቃላቸው ልባቸውን ይገልጣልና (ማለትም፣ ሁለቱም ወገኖች፣ ማቴ. 12:33-37፤ ሉቃስ 6:45)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 50፥1-6**

**የአሳፍ መዝሙር።**
**[1]የአማልክት አምላክ እግዚአብሔር ተናገረ፥**
**ከፀሓይም መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ ምድርን ጠራት።**
**[2]ከክብሩ ውበት ከጽዮን**
**እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል።**
**[3]አምላካችን ይመጣል ዝምም አይልም**
**እሳት በፊቱ ይቃጠላል፥**
**በዙሪያውም ብዙ ዐውሎ አለ።**
**[4]በላይ ያለውን ሰማይን**
**ምድርንም በሕዝቡ ለመፍረድ ይጠራል**
**[5]ከእርሱ ጋር ለመሥዋዕት ኪዳን የቆሙትን**
**ቅዱሳኑን ሰብስቡለት።**
**[6]ሰማያት ጽድቁን ይናገራሉ፥**
**እግዚአብሔር ፈራጅ ነውና። ሴላህ**

**50፥1-6** ይህ አንጓ የሚያሳየው ያህዌ ጻድቅ ፈራጅ መሆኑን ነው (ዝከ. ቁ. 6)። አብዛኛው የዚህ መዝሙር ምናባዊ ምስል የፍርድ ቤት ትዕይንት ነው።
1. ምድርን ይጠራል፣ ቁ. 1፣4
2. ሁለቱ ዘላለማዊ ምስክሮች — ሰማይና ምድር (ዘዳ. 4:26፤ 30:19፤ 31:28፤ 32:1)፣ ቁ. 4
3. እግዚአብሔር ራሱ ፈራጅ ነው፣ ቁ. 5
4. ባንተ ላይ እመሰክርብሃለሁ፣ ቁ. 7፤ መላው ዓለም፣ ሰማይና ምድር፣ እንዲመሰክሩ መጠራታቸውን ተገንዘብ፣ ያህዌ የኪዳን ሕዝቡን በከሰሰበት ጉዳይ

**50፥1** ጥቅም ላይ የዋሉትን የመለኮት ስሞች/መጠሪያዎች ተገንዘብ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡1 ላይ)፡
1. *ኤል*፣ ቁ. 1 – ቢዲቢ 42፣ የእግዚአብሔር አጠቃላይ ስም፣ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ከ "ብርቱ መሆን" ሥር፣
2. *ኤሎሂም*፥ ቁ. 1፣2፣3፣6፣7 (ሁለቴ)፣ 14፣16፣23 – ቢዲቢ 43፣ እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ፣ ሰጪ፣ እና መጋቢ፣ ለሕይወት ሁሉ
3. *ያህዌ*፣ ቁ. 1 – ቢዲቢ 217፣ ኪዳን ሰጪው አምላክ፣ እግዚአብሔር እንደ አዳኝ፣ ተቤዢ፣ (ቁ. 5)
4. ኤሊዮን፣ ቁ. 14 – ቢዲቢ 751 II፣ ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 46:5 ላይ፣ "ልዑሉ" (ዘዳ. 32:8፤ መዝ. 9:2፤ 21:7፤ ወዘተ.)
5. ኤሎአህ፣ ቁ. 22 – ቢዲቢ 42፣ የኤሎሂም ነጠላ (ባብዛኛው ኢዮብ ላይ)

ሊሆን የሚችለው ቀዳሚዎቹ ሦስቱ አንድ መጠሪያ እንደሚያበጁ ነው (ኢያ. 22:22)። LXX፣ አኢመቅ፣ እና ኤቢ (ገጽ 304) እንደሚሉት፣ "አምላክ (ኤል) አማልክት (ኤሎሂም) ያህዌ ነው።" አንዳንድ ጽሑፋዊ/ሥነ-መለኮታዊ ምክንያቶች አሉ፣ እነዚህን ሦስት ስሞች በተከታታይነት ለማያያዝ፣ እሱ ግን ለዘመናዊዎቹ ጠፍቶባቸዋል።

◘ **"ምድር"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል *ኤሬትስ* ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 75፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 1:2 ላይ)። ትይዩው ቃል፣ "ዓለም" (ቢ.ዲ.ቢ. 385፤ መዝ. 9:8፤ 18:15፤ 19:4፤ 24:1፤ 33:8፤ 50:12)፣ በብዛት ጥቅም ላይ የዋለው መዝሙር እና ኢሳይያስ ላይ ነው።

◘ **"ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያዋ ድረስ"** ሐረጉ (መዝ. 113:3) ለሁለንተናዊነት ዘይቤ ነው፣ እንደ "ከምስራቅ እስከ ምዕራብ።" ሰዎች ሁሉ ወደ ያህዌ ችሎት ተጠርተዋል። ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ወደ አኪ የመጣው እንደ

1. የበጎቹ እና የፍየሎቹ ፍርድ፣ ማቴ. 25:31-46
2. የክርስቶስ የፍርድ ወንበር፣ 2 ቆሮ. 5:8
3. የታላቁ ነጭ ዙፋን ፍርድ፣ ራዕ. 20:11-15

ይህም 1 ቆሮ. 15:25-28 ላይ ተጠቅሷል። ሰዎች ለእግዚአብሔር ምላሽ ይሰጣሉ፣ ስለ ሕይወት ስጦታ መጋቢነታቸው!

**50:2 "ጽዮን"** እዚህ የእግዚአብሔር ከተማ፣ ኢየሩሳሌም፣ የተመለከተችው እንደ "የውበት ፍጻሜ" ነው። መዝ. 48:2 ላይ "ለእይታ ያማረች፣ የምድር ሁሉ ደስታ" በሚል ተጠርታለች። እነዚህ ሁለቱም ገላጭ ሐረጋት ተደባልቀዋል፣ ሰቆ. 2:15 ላይ። ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 2:6፤ 9:11፤ 20:1 ላይ።

◘ **"እግዚአብሔር ግልጽ ሆኖ ይመጣል"** ይኸው ተመሳሳይ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 422፣ ኬቢ. 424፣ *ሂፊል ተተኳሪ*) ጥቅም ላይ ውሏል መዝ. 80:1 (*ሂፊል ተተኳሪ*) እና መዝ. 94:1 (ደግሞ *ሂፊል ተተኳሪ*)። መዝሙር 49:14 ላይ የብርሃኑ ምናብ የተለያዩ ነገሮችን እንዴት እንደሚጠቅስ ዘርዝሬአለሁ። እግዚአብሔር የዓለም ብርሃን ነው (መዝ. 27:1፤ ኢሳ. 60:1-3፣19-20) እና ልጁም ደግሞ (ዮሐንስ 8:12፤ 12:35)። በእነርሱ ምክንያት እንዲሁ የእነርሱ ታማኝ ተከታዮች ደግሞ (ማቴ. 5:14፤ 6:23፤ ዮሐንስ 12:36)።

**50:3** ይህ ግሥ የሚጀምረው በሁለት ተጽዕኗዊዎች ነው ("ሊሆን ይችላል…")።

1. አምላካችን ይመጣል – ቢ.ዲ.ቢ. 97፣ ኬቢ. 112፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ* በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ዝምምም አይልም – ቢ.ዲ.ቢ. 361፣ ኬቢ. 357፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ* በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

የፍርድ ቀን ደርሷል እናም የእግዚአብሔር ሰዎች በመጀመሪያ ይጠየቃሉ (ኤር. 25:29፤ 1ጴጥ. 4:17)።

◘ **"እሳት በፊቱ ይቃጠላል"** እሳት ዘወትር የሚያያዘው ከ

1. ቅድስና/ንጽሕና የአምላክ – ዳን. 7:10
2. ማጥሪያ – ዘኍ. 31:23
3. ፍርድ – ሌዋ. 10:2፤ ዘኍ. 16:35

ከ "እሳት" ጋር ስለተያያዘው ሙሉ ምናባዊ ምስያ ዝርዝር ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 11:6 ላይ።

በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ እሱ የሚያያዘው በምድር አካላዊ መግለጫ ነው፣ ቅዱሱ እግዚአብሔር በሚደርስበት ጊዜ ("ይመጣል፣" ቁ. 3ሀ) የወደቀው ፍጥረቱ (መዝ. 18:7-15፤ 97:1-6)።

**50:4 "ሰማይ… ምድር"** እነዚህ ሁለቱ ተጠቃሽ ምስክሮች ናቸው (ዘኍ. 35:30፤ ዘዳ. 17:6፤ 19:15) ያህዌ ሕዝቡን ወደ ፍርድ ቤት ሲወስድ (ዝከ. 50:4-5፣7፣16-21፣22-23)። እነዚህ የሚወክሉት የመጀመሪያ ሁለቱን ተፈጣሪ ነገሮች ነው (ማለትም፣ ምድርና ከባቢ አየሯን)።

**50:5 "መሰብሰብ"** ይህ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 62፣ ኬቢ. 74፣ ቃል ያልተጠናቀቀ) ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ "መጥራት" ከሚለው ጋር ትይዩ ነው (ቁ. 1፣4)። "ቅዱሳንን" እንደሆነ ተገንዘብ (ማለትም፣ የኪዳን ሕዝቦች) እነርሱም ለፍርድ ቀን የተሰበሰቡ (ማለትም፣ "የክርስቶስ የፍርድ ወንበር" 2 ቆሮ. 5:10 ደግሞ ለአማኞች ነው ለማያምኑት ሳይሆን)።

◘ አምልኮ-ተኮር ተከታዮች እንዴት እንደተገለጹ ተገንዘብ።

1. ቅዱሳኖቼ፣ ቁ. 5
2. ከእኔ ጋር ቃል ኪዳን ያደረጉ፣ በመሥዋዕት፣ ቁ. 5
3. ሕዝቤ ሆይ፣ ቁ. 7 (ኪዳናዊ ቃል)
4. እነርሱም እንዲያደርጉ ታዘዋል (ቁ. 14-15)
   ሀ. የምስጋና መሥዋዕት እንዲያቀርቡ (ቃል ተተኳሪ)
   ለ. መሐላቸውን በልዑሉ እንዲያደርጉ (ፔል ተተኳሪ)
   ሐ. በመከራ ጊዜ ያህዌን እንዲጠሩ (ቃል ተተኳሪ)

◘ **"ቅዱሳኖቼ"** ይህ ቃል/መጠሪያ (ቢ.ዲ.ቢ. 339) በመዝሙር ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል፣ ታማኝ ተከታዮችን ለመጥቀስ (ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 4:3፤ 12:1፤ 16:10፤ 18:25፤ 30:4፤ 31:23፤ 32:6፤ 37:28፤ 43:1፤ 52:9፣ ላይ፣ ወዘተ.)። መዝሙር 16:10 ላይ እሱ የሚጠቅሰው በዐቢይ ምድብ ነው፣ እንዲሁም አኪ የሚጠቅሰው ለመሢሑ ነው።

እዚህ የሚያመለክተው እስራኤላውያንን ነው፣ እነርሱም በአምልኳዊ መሥዋዕት ላይ እጅግ የሚያተኩሩ፣ እናም በግላዊ እምነት እና የሕይወት ስልት መልካምነት ላይ እምብዛም የሆኑ።

◘ **"ለእኔ"** የፍርድ ትዕይንት እንኳ ቢሆን ለቀረበ ኅብረት ጥሪ ነው። ለኃጢአተኛ የፍርድ እና የመለየት ጥሪ ነው! ለአምልኮ-ተኮር አማኞች የለውጥ ጥሪ ነው።

**50:5 "ኪዳን"** ይህ ዋነኛ ሥነ-መለኮታዊ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 136) ዕብራይስጣዊ አይደለም። ጽንሰ-ሐሳቡ በተሻለ የሚገልጸው የኪዳንን አምላክ እና ትዕዛዝ፣ ቀጣይነት ያለው፣ ኃላፊነት ያለው ምርጫ፣ በሰብዓዊ ፍጡራን አኳያ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 25:10 ላይ)።

▣ **"በመሥዋዕት"** ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ መሥዋዕት በሜሶፖታሚያ እና እስራኤል እና ጠቀሜታው

(እነዚህ ማስታወሻዎች የእኔ የብኪ ጥናት ማስታወሻዎች ክፋይ ናቸው። ደግሞም ኒዶቴ ላይ ያለውን ሠንጠረዥ እይ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 1020-1021)

I. የአምልኮ ሕግጋት በሜሶፖታሚያ
 ሀ. መሥዋዕት በቀዳሚነት ለአማልክት የሚቀርብ ሙብል ነው። መሠዊያው የአማልክት ጠረጴዛ ነበር፣ እዚያም ሙብሉ ይቀመጣል። ከመሠዊያው አጠገብ የዕጣን ምድጃ አለ፣ እሱም የአማልክትን ቀልብ ለመማረክ። አምልኮታዊ አንድምታ በደሙ ውስጥ አልነበረም። ሰይፍ ያዡ የእንስሳውን ጉሮሮ ይቆርጣል። ሙብሉም ለአማልክቱ፣ ለካህን-ንጉሡ፣ እና ለአሳላፊዎቹ (ለተገኙት ሰዎች) ይከፋፈላል። መሥዋዕት አቅራቢው ምንም አይቀበልም።
 ለ. የሚያስተሰርይ መሥዋዕት አልነበረም።
 ሐ. ሕማም ወይም ሥቃይ ከአማልክት የሆነ ቅጣት ነበር። እንስሳ እንዲመጣ ይደረግና ይጠፋል፤ ይህም ለመሥዋዕት አቅራቢው እንደ ምትክ ይሆናል።
 መ. የእስራኤል የአምልኮ ሥርዓት ልዩና በባሕርዩ የተለየ ነበር። እሱም በዋነኛነት ግለሰቡ የሥራውን ፍሬ ለእግዚአብሔር መልሶ የሚያቀርብበት ነበር፣ በአስፈላጊው ምግብ መልኩ (ዘፍ. 4፡1-4፤ 8፡20-22)።

II. የአምልኮ ሥርዓት ሕግጋት በከነአን (ከእስራኤል ጋር እጅግ ተመሳሳይ)
 ሀ. ምንጮች
  1. መጽሐፍ ቅዱሳዊ አስረጅዎች
  2. ፍንቄያዊ ሥነ-ጽሑፍ
  3. የራስ ሻምራ የድንጋይ ጽሑፎች ከዑጋሬት፣ የከነአንን አማልክት እና አፈ-ታሪኮችን በተመለከተ፣ ከ1400 ቅ.ል.ክ አካባቢ
 ለ. የእስራኤልና የከነአን መሥዋዕት እጅግ ተመሳሳይ ናቸው። ሆኖም፣ ምንም ዓይነት የተቀመጠ አጽንዖት የለም በከነአን መሥዋዕት በሚቀርበው ደም።

III. የግብፅ የአምልኮ ሥርዓት ሕግጋት
 ሀ. መሥዋዕት ይቀርባል፣ ግን የተጋነነ አይደለም።
 ለ. መሥዋዕት እጅግም ጠቀሜታ አልነበረውም፣ ነገር ግን የመሥዋዕት አዝማሚያ ነበር።
 ሐ. መሥዋዕት የሚደረገው የአማልክትን ቍጣ ለማስቆም ነበር።
 መ. መሥዋዕት አቅራቢው ትድግና ወይም ይቅርታን እንዲያገኝ ተስፋ ያደርግ ነበር።

IV. የእስራኤል የመሥዋዕት ሥርዓት እና የእስራኤል መሥዋዕት ከከነአን ጋር ስለ መቀራረቡ፣ ምንም እንኳ ከእነርሱ ጋር ሙሉ ለሙሉ ባይቀራረብም።
 ሀ. የመግለጫ ሐረጎች
  1. መሥዋዕት የሰው ልጅ እግዚአብሔርን ሲፈልግ በድንገተኝነት የሚያቀርበው መግለጫ ነበር።
  2. የብኪ ሕግጋት እነርሱም መሥዋዕትን የሚያዙት መሥዋዕትን አነሣስተዋል ማለት አይቻልም (ዘፍ. 7፡8፤ 8፡20)።
  3. መሥዋዕት የሚቀርብ ነበር (እንስሳ ወይም ዕጽዋት)።
  4. መሥዋዕት የሚቀርበው በሙሉም ሆነ በከፊል በመሠዊያው ላይ መጥፋት ነበረበት፣ ለእግዚአብሔር በተለየ ስፍራ።
  5. መሠዊያ የመሥዋዕት ስፍራ ነበር እናም በተምሳሌትነት የመለኮት መገኛ።
  6. መሥዋዕት የውጫዊ አምልኮ ድርጊት ነበር (በውጭ የሚደረግ የጸሎት ትዕይንት)።
  7. የመሥዋዕት ፍች "ትዕይንታዊ ጸሎት" ወይም "የአምልኮ ሥርዓታዊ ጸሎት።" የአምልኮ ሥርዓቱ ጠቀሜታና እኛ በእሱ ላይ ያለን ባህላዊ ቅድመ-አቋም፣ በጎርደን ጂ. ዌንሀም ላይ ተገልጿል (ቲንዳሌ፣ ነምበርስ፣ ገጽ 25-39)። ሌዋውያን እና ዘኍልቁ ሁለቱም በርካታ መጠን ያለው የዚህ ዓይነት ነገር ይዘዋል፣ ይኸውም ጠቃሚነቱን የሚያመላክት፣ ለሙሴ እና እስራኤል።
 ለ. መሥዋዕቱ የሚያካትተው
  1. ለእግዚአብሔር ስጦታ
   ሀ. ምድር ሁሉ የጌታ መሆኗን እውቅናን የሚያካትት
   ለ. ሰው ያለው ሁሉ፣ የእግዚአብሔር እንደሆነ
   ሐ. ስለዚህ፣ ሰዎች ለእግዚአብሔር ስጦታ ማምጣታቸው ተገቢ ነው
   መ. እሱ የተለየ ዓይነት አስተዋጽዖ ወይም በረከት ነበር። እሱም አንድ ሰው ለሕልውናው ሲል የሚያደርገው ዓይነት ነገር ነበር። እሱም አንድ ነገር ከመስጠት ያለፈ ነበር፣ እሱም የሚያስፈልገው ዓይነት ነበር። እሱም የራሱን አካል ለእግዚአብሔር እንደ መስጠት ነበር።
   ሠ. ስጦታውን በማጥፋት መልሶ መጠየቅ አይቻልም።
   ረ. የሚቃጠል መሥዋዕት የማይታይ ይሆናል፣ ወደ እግዚአብሔር መኖርያ ያቀናል
   ሰ. የቀድሞዎቹ መሠዊያዎች የሚተከሉት እግዚአብሔር በታየባቸው ቦታዎች ላይ ነበር። መሠዊያው እንደ ቅዱስ ስፍራ ይቆጠራል፣ ስለዚህ፣ መሥዋዕቱ እዚያ ይመጣል።
  2. የአንዱ ሙሉ ሕይወት ለእግዚአብሔር የተሰጠ መሆኑን መግለጫ
   ሀ. የሚቃጠል መሥዋዕት ከሦስቱ የፍቃድ መሥዋዕቶች አንደኛው ነው
   ለ. ሙሉው እንስሳ የሚቃጠለው ለእግዚአብሔር ያለንን ጥልቅ ከበሬታ ለመግለጽ ነው
   ሐ. ይህ እጅግ ገላጭ የሆነ ስጦታ ነው፣ ለእግዚአብሔር
  3. ኅብረት ከእግዚአብሔር ጋር
   ሀ. ተግባቦታዊ ገጽታ ያለው መሥዋዕት

ለ. የሰላም መሥዋዕት አንድ ምሳሌ ሊሆን ይችላል፣ እሱም እግዚአብሔርና ሰው ኅብረት እንዳላቸው ተምሳሌት የሚሆን
ሐ. መሥዋዕት የሚደረገው ይሄንን ኅብረት ለማግኘት ነበር

4. የኃጢአት ማስተሠርያ
ሀ. ሰው ኃጢአት ሲሠራ እግዚአብሔርን ሊጠይቅ ይገባል፣ ግንኙነቱ እንዲመለስለት (ኪዳን) እሱም ሰው የሰበረው
ለ. የአንድነት መብል አይኖርም፣ በኃጢአት መሥዋዕት ጊዜ፣ በተሰበረው ግንኙነት ሳቢያ
ሐ. የደሙ ጠቀሜታ
(1) በመሠዊያው ላይ ይሆናል፣ ስለ ሰው
(2) በመሸፈኛው ላይ ይሆናል፣ ስለ ካህኑ
(3) በምሕረት ማኖሪያው ላይ ይሆናል፣ ለሊቀ ካሕኑና ለሕዝቡ (ሌዋውያን 16)
መ. ሁለት ዓይነት የኃጢአት መሥዋዕቶች ነበሩ። ሁለተኛው የበደል መሥዋዕት ወይም የመተላለፍ መሥዋዕት ይባላል። በእሱም ላይ ተላላፊው ወደ እስራኤላውያን ወገኖቹ ይመልሳል፣ የተወሰደውን ወይም የተጎዳውን፣ በእንስሳ መሥዋዕት በኩል።
ሠ. ምንም ዓይነት መሥዋዕት አልነበረም፣ ቀድሞ ለታሰበበት ወይም ሆን ተብሎ ለተሠራ ኃጢአት፣ ሌዋ. 4፡2፣22፣27፤ 5፡15-18፤ 22፡14

V. የሌዋውያን ደንቦች፣ ለተለያዩ መሥዋዕቶች
ሀ. ሌዋውያን 1
1. የመግቢያ መግለጫ፣ "እግዚአብሔርም ሙሴን ተናገረው፣" 1፡1-2፤ 4፡1፤ 5፡14፤ 6፡1፣19፤ 7፡22፣ 28
ሀ. ከእንስሶቹ ወይም ከመንጋው
ለ. "መቼ" (ጊዜ) ቁ. 2፣ የሚያሳየው ይህ አስገዳጅ አለመሆኑን ነው፣ የፍቃድ እንጂ
2. የሚቃጠል መሥዋዕት፣ ቁ. 3-17 (6፡8-13)
ሀ. መሠዊያ
(1) የነሐስ መሠዊያ፣ እሱም ደግሞ የሚቃጠል መሥዋዕት መሠዊያ የሚባል፣ በመገናኛው ድንኳን በር ያለ መሠዊያ ወይም የግራር እንጨት መሠዊያ፣ በነሐስ የተሸፈነ (ዘጸዓት 27)
(2) ይህም የላቀ ያደርገዋል፣ ከዕጣን መሠዊያ (የወርቅ መሠዊያ) በቅዱስ ስፍራ (ዘጸአት 30)
(3) ከነሐስ መሠዊያው ላይ የከሰል ፍም ተወስዶ ዕጣን መሠዊያው ላይ ይደረጋል
(4) የነሐስ መሠዊያው ያለው ከመገናኛው ድንኳን መግቢያጋ ልክ መካከሉ ላይ ነው
(5) መሠዊያው ቀንዶች አሉት፣ እሱም እጅግ የተቀደሰ ክፍል ነው። ደሙ ወደ ቀንዶቹ ይደረጋል (ዘጸ. 30፡10)።
(6) ቀንዶቹ ሊሆኑ የሚችሉት፡
(ሀ) ለእጅ ተምሳሌት መሥዋዕቱን ከፍ አድርጎ ለመያዝ
(ለ) የብርታት ወይም የላቀ ኃይል ተምሳሌት (ዘዳ. 33፡17፤ 2 ሳሙ. 22፡3።)
(ሐ) ኋላ ላይ፣ ማንም የመሠዊያውን ቀንድ ከያዘ ደኅንነቱ የተጠበቀ ይሆናል፣ ጉዳዩ በፍርድ ቤት እስኪወሰን ድረስ (1 ነገ. 1፡50-51፤ 2፡28)
ለ. መሥዋዕት
(1) ወይፈን ነውር የሌለበት እሱም በቀዳሚነት የተጠቀሰ፣ ከጠቀሜታውና ከዋጋው አኳያ፣ ሌዋ. 1፡3
(2) ተባዕት ፍየል ወይም በግ፣ 1፡10
(3) ርግቦች ወይም ፒግአንስ ፣ 1፡14 (ለድሀ የታሰበ)
ሐ. የሚቃል መሥዋዕቱ ስፍራ በመገናኛው ድንኳን በር ላይ ነበር
መ. እጅ መጫን፣ ይህ የሚሆነው ለወይፈኖች ብቻ ነበር፣ ለፍየሎች፣ ለበጎች፣ ወይም ለወፎች ሳይሆን፣ 1፡4
(1) መሥዋዕት አቅራቢው ራሱ ይሄንን ያደርጋል (ካህኑ ሳይሆን)
(2) ብዙዎች የሚያስቡት እሱ ተምሳሌታዊ ድርጊት መሆኑን ነው፣ ስለ መተላለፍ በደል
(3) አንዳንዶች የሚያምኑት እሱ ማለት
(ሀ) ይህ እንስሳ የመጣው ከዚህ ግለሰብ ነው
(ለ) መሥዋዕቱ መቅረብ የሚኖርበት በአቅራቢው ስም ነው
(ሐ) የዚህ መሥዋዕት ፍሬ የሚገባው በእንስሳው ላይ እጁን በጫነው ላይ ነው
ሠ. እርድ
(1) ወይፈን — "በጌታ ፊት፣" መሥዋዕት በሚያቀርበው ሰው። መሥዋዕት አቅራቢው እንስሳውን ማረድ፣ ቆዳውን መግፈፍ፣ እና መቆራረጥ ይኖርበታል። የካህኑ ሚና (ከሕዝብ መሥዋዕት ማቅረብ ጉዳይ በስተቀር) የሚጀመረው ሰውየው እንስሳውን ወደ መሠዊያው ሲያመጣ ነው።
(2) በግ ወይም ፍየል፣ 1፡11 — "ከመሠዊያው በስተሰሜን፣ በጌታ ፊት።" ይህ የተወሰነው የተለየ ስፍራ ነው፣ ለእነዚህ አነስተኛ እንስሳት።
(3) ወፍ — "ካህኑ ይህን መሥዋዕት አርዶ ያቀርባል።" መሥዋዕት አቅራቢው የወፉን ላባ ማስወገድ ይኖርበታል።
ረ. የደም አያያዝ
(1) እንስሳት
(ሀ) ካህኑ በመሠዊያው ላይ ደሙን ያፈሳል፣ እናም በመሠዊያው ዙሪያ ይረጨዋል።
(ለ) የእንስሳ ሕይወት ደሙ ነው (ዘፍ. 9፡4፤ ሌዋ. 17፡11)። ሕይወት ቀደም ብሎ የእግዚአብሔር ነው፣ ስለዚህ፣ ደም የትኛውንም ዓይነት የሰውየውን ስጦታ ክፍል አይወክልም።
(ሐ) የወፍ ደም በመሠዊያው ላይ ይቀዳል፣ እናም በእሳት አይቃጠልም።
ሰ. የሥጋው አያያዝ
(1) ወይፈን፣ ሌዋ. 1፡6
(ሀ) መሥዋዕት አቅራቢው የመሥዋዕቱን ቆዳ ይገፍፋል። ካህኑ ቆዳውን ያኖረዋል (ሌዋ. 7፡8)

(ለ) መሥዋዕት አቅራቢው በየብልቱ ይቆራርጠዋል
(ሐ) ካህኑ መሥዋዕቱን መሠዊያው ላይ ያኖረዋል፣ በሕይወት እንዳለ፣ በተስተካከለ መልኩ
(መ) እግሩና የሆድ ዕቃው በሳህን ላይ ባለው ውኃ ይታጠባል
(ሠ) ካህኑ ሙሉውን እንስሳ በመሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል

3. የሚቃጠል መሥዋዕት የሚቀርብበት ሁነት
   ሀ. የማደሪያው ድንኳን፣ በዓል፣ የተለየ ስፍራ
   ለ. የመታደስ ቀን
   ሐ. የሳምንታት በዓል፣ በኩራት፣ ወይም በዓለ ሃምሳ
   መ. የመለከት በዓል
   ሠ. ነዶ መወዝወዝ (ሌዋውያን 23)
   ረ. የቂጣ በዓል፣ ፋሲካ
   ሰ. የወራት መጀመሪያ፣ አዲስ ጨረቃ
   ሸ. ሰንበት
4. የሚቃጠል መሥዋዕት ጠቀሜታ
   ሀ. ለእግዚአብሔር ስጦታ
   ለ. እሱም እጅግ ዋጋ እንዳለው የመሥዋዕት ዓይነት ይቆጠራል
   ሐ. እሱም እንደ ኃጢአት ጽንሰ-ሐሳብ ባጠቃላይ ይቆጠራል፣ ወይም ምስጋና ማቅረብ
   መ. ለመሥዋዕታዊ ሐሳብ እጅግ የተሻለው ወካይ
   ሠ. ለአንዱ ሕይወት ተምሳሌታዊ መሥዋዕት
   ረ. የአንድ ግለሰብ ሕይወት ለእግዚአብሔር አገልግሎት ፍጹም መቀደስን (መሰጠትን) ይወክላል
   ሰ. የመሥዋዕቱ የዋጋ ደረጃ
      (1) ወይፈን
      (2) በግ — ፍየል
      (3) አዕዋፍ
   ሸ. ይህም የመንፈሳዊ መሻት ንቃት ያለው እግዚአብሔርን መቅረብ እንደሚችል ያሳያል። እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ስጦታዎችን አድርጓል።
5. ልዩ ትእዛዝ ለካህን፣ ሌዋ. 6፡8-12
   ሀ. የሚቃጠል መሥዋዕት ሌሊቱን ሁሉ በመሠዊያው ምድጃ ላይ ይኖራል
   ለ. እሳት እንደነደደ ይቀጥላል፣ በሚቃጠለው መሥዋዕት
   ሐ. የካህኑን ቀሚስ በተመለከተ የተካተቱት መመሪያዎች
   መ. አመዱን ስለ ማስወገድ የተካተቱት መመሪዎች

ለ. ሌዋውያን 2፡1-16 (6፡14-23)
1. መግቢያ
   ሀ. ይህ ምዕራፍ የሚመለከተው የእህል መሥዋዕት ነው
   ለ. የእህል መሥዋዕት "ስጦታ" ከሚለው ሥር ፍች ነው። እሱም ሙያዊ ቃል ሆኗል፣ እንስሳ ላልሆነ፣ ወይም ዕጽዋት ስጦታዎች።
   ሐ. ከግዞት በኋላ የእህል ቍርባኑ የሚቀርበው ለሚቃጠል መሥዋዕት እና ለሰላም መሥዋዕት ተጨማሪ ሆኖ ነው፣ ራቢዎችም እጅግ ደሀ ለሆነ ብቻውን መቅረብ እንደሚችል ይገልጻሉ።
   መ. የጨው ኪዳንም ደግሞ ተጠቅሷል፣ ዘኍ. 18፡19 እና 2 ዜና 13፡5 ላይ። ጨው የኮምጣጤ ተቃራኒ ነው። እሱም እንደ እግዚአብሔር ኪዳን ተምሳሌት ጥቅም ላይ ይውላል፣ ምክንያቱም እሱ የማይበላሸና የማያበቃ በመሆኑ።
2. የእህል ቍርባን የሚያካትተው የአንዱ የድካሙ ፍሬ ለእግዚአብሔር መሰጠቱን ነው።
   ሀ. እሱም ለእግዚአብሔር ስጦታ ነው፣ ከሕዝቡ የዕለት ሙብል ላይ።
   ለ. እሱ ባጠቃላይ ተጨማሪ ነው (በተለይም ከድኅረ ግዞት ቀናት በኋላ) ለሚቃጠል ወይም ለሰላም መሥዋዕት።
   ሐ. መሥዋዕት እግዚአብሔር የሰጠው ነው ለካህኑ። አነስተኛ ክፍሉ ብቻ ይቃጠላል፣ ለሙሉው መታሰቢያ እንዲሆን።
   መ. "መታሰቢያ" የሚለው ቃል የሚገልጸው መሥዋዕት የሚሆነውን ክፍል፣ ወይም ያንን ሙሉውን ወደ እግዚአብሔር ፊት የሚቀርበውን ክፍል ነው።
   ሠ. የአዲስ ኪዳን ጽንሰ-ሐሳብ የጌታ ራት እንደ "መታሰቢያ" መሆኑ ይሄንን የብሉይ ኪዳን ጽንሰ-ሐሳብ ይገልጻል።
   ረ. በ"ቅድስት" እና "ቅድስተ ቅዱሳን" በሚሉት ቃላት መካከል ያለው ልዩነት፡
      (1) "ቅዱስ" — ካህኑና ቤተሰቡ ሊመገቡት ይችላሉ፣ በየትኛውም ንጹሕ ስፍራ
      (2) "ቅድስተ ቅዱሳን" — በካህናት ብቻ ነው የሚበላው፣ በመገናኛው ድንኳን ስፍራ
3. ዓይነቶች
   ሀ. ያልተጋገረ ዱቄት (ለሀብታም)፣ ሌዋ. 2፡1-3
   ለ. የተጋገሩ ሙልሙሎች ወይም ኅብስት፣ ሌዋ. 2፡4-11
   ሐ. የበቆሎ እሸት ወይም የስንዴ ነዶ (ለደሀ)፣ ሌዋ. 2፡12-16
      (1) ያልተጋገረ ዱቄት ከፍያለ መባ ነበር። እሱም እጅግ የተሻለው የስንዴ ዱቄት ነበር።
      (2) የተጋገረ ኅብስት
         (ሀ) ዘይት አንደኛው ውህድ ነበር
         (ለ) በምድጃ ላይ ይዘጋጃል፣ 2፡4
         (ሐ) በመጋገሪያ ብረት፣ 2፡5
         (መ) በሸክላ መጥበሻ፣ 2፡7።

(3) የበቆሎ እሸት ወይም የስንዴ
(ሀ) መጠበስ ይኖርበታል
(ለ) በየመጠኑ ይቆራረሳል
(ሐ) በእንግዶች ፊት እንደሚቀርብ ምግብ ይዘጋጃል
4. ውህዶች
ሀ. መልካም ዱቄት ነውር ከሌለበት እንስሳ ጋር ተደርጎ
ለ. ዘይት የብልጽግና ተምሳሌት ነው፣ እና ስለዚህ፣ የእግዚአብሔር መገኘት ተምሳሌት
(1) ለምግብ፣ ለመሥዋዕት፣ ለመድኃኒት፣ እና ለመቀባት ጥቅም ላይ ይውላል
(2) ዘይትን መጠቀም የሚሆነው የዘይትን ቁርባን ለመተካት ነው
ሐ. ዕጣን ከሕንድ ወይም ከዓረብ ነበር
(1) እንደ እጅግ ንጹሕ ነገር ይታያል፣ በአስደናቂ መዓዛ
(2) የጸሎትና የምስጋና ተምሳሌት ነው
መ. ጨው
(1) ሕይወት ሰጪ ብሎም የጠባቂነት ይዘት (ከመበስበስ)
(2) ምናልባትም ባመዛኙ ለማዕድ ኅብረት ከጠባቂነት ይልቅ
ሠ. ያልተካተቱት ነገሮች
(1) ቡኮ አልተካተተም፣ 2፡11
(ሀ) ከመቡካቱ የተነሣ ሊሆን ይችላል
(ለ) ቡኮ ከመበስበስ ጋር ይያያዛል
(ሐ) ከበኵራት ጋር ሊቀርብ ይችላል እንዲሁም ለካህኑ
(2) ማር አልተካተተም
(ሀ) ፈሳሹ ከፍራፍሬ ነው እንጂ ከንብ ማር አይደለም
(ለ) ለከነአን የአምልኮ ሥርዓት በመቅረቡ ሊሆን ይችላል
5. የመባው አምልኮ ሥርዓት
ሀ. እሱም ወደ ካህኑ ይቀርባል፣ ሙሉውን ሥነ ሥርዓት ወደሚያካሂደው (2፡2፣ 9፣ 16)
ለ. የመባውን ከፊል ካህኑ ይመገበዋል፣ በመቅደሱ። እሱም እጅግ ቅዱስ ነው።
6. ጠቀሜታው
ሀ. ከዝቅተኛው እስከ ከፍተኛው ይቀርባል
ለ. ከፊሉን ማቃጠሉ አንዱ የሥራውን ፍሬ ከፊል ለእግዚአብሔር ማቅረቡን ይወክላል
ሐ. ግልጽ የሆነ ፍችው
(1) የሚቃጠል መሥዋዕት — የአንዱ የሕይወት መቀደስ
(2) የምግብ መሥዋዕት — ከአንዱ የዕለት ሥራው የተሰጠ
7. ለእህል ቍርባን የተለየ መመሪያ፣ ሌዋ. 6፡14-23
ሀ. በመሠዊያው አጠገብ የሚቀርብ
ለ. ከሥራው ፍሬ የሚቀርበው መባ ለእግዚአብሔር ስጦታ ነው፣ በእውነታው ግን የክህነት ሥርዓቱን የሚደግፍ ነው
ሐ. ሌዋውያን 3፡1-17 (7፡13-34)፣ የሰላም መሥዋዕት
1. መግቢያ
ሀ. ለምን
(1) የአንድነት መባ
(2) የኪዳን መሥዋዕት
(3) የተጠቃለለ መባ
(4) የማጠቃለያ መሥዋዕት
ለ. እሱም የሚገልጸው ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብን ነው፣ ከእግዚአብሔር፣ ከቤተሰብ፣ ከጓደኞች ጋር ካለው ኅብረት የተነሣ፣
ሐ. እሱም ዘወትር የመጨረሻ ድርጊት ነበር፣ ተለጣጣቂ ከሆኑት መሥዋዕት፣ እነርሱም መታረቅን ከሚያመጡት
መ. የሚቃጠለው መሥዋዕት የመታዘዝን ውድነት ሲገልጽ፣ የሰላም መሥዋዕት ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆነው ኅብረት የሚኖረውን ደስታና ፍስሐ ይገልጻል
ሠ. ተባዕት ወይም እንስት ግን ነውር የሌለባቸው
ረ. የመሥዋዕት ልዩነት
(1) ከመንጋው፤ ወንድ ወይም ሴት
(2) በበግና በፍየል መካከል ያለው ልዩነት በበግ ላት ላይ ባለው ስብ ነበር
(ሀ) ከመንጋው የበግ ጠቦት — ወንድ ወይም ሴት
(ለ) ከመንጋው ፍየል — ወንድ ወይም ሴት
2. የአምልኮ ሥርዓት
ሀ. መሥዋዕት አቀራረብ
(1) በመሥዋዕቱ ላይ እጅ መጫን
(2) በመገናኛው ድንኳን ደጅ ላይ ማረድ
(3) የመሥዋዕት መለያው እንደሚቃጠል መሥዋዕት ዓይነት ነበር
(4) በመሠዊያው ዙሪያ ደም መርጨት
(5) የተመረጡ ብልቶችን በመሠዊያው ላይ ለእግዚአብሔር ማቃጠል

(ሀ) ስብ (የበግ ላት) የብልጽግና ምሳሌ
(ለ) ኩላሊት፣ ጉበት የፍቃድና የስሜቶች ተምሳሌት
(ሐ) በመሥዋዕት አቅራቢው የሚቃጠል መሥዋዕት ላይ የሚገኝ ስብ አካል፣ ወይም በማለዳ የበግ መሥዋዕት

ለ. የምስጋና መሥዋዕት የሚያካትተው (ሌዋ. 7፡11-14)

(1) ቂጣ ኅብስት በዘይት የተለወሰ
(2) ቂጣ ሙልሙል ዘይት የተቀባ
(3) መልካም ዱቄት ዘይት የተለወሰ

3. የካህኑ ድርሻ፣ ሌዋ. 7፡28-34

ሀ. ፍርምባው ለካህኑ ይሰጣል ለሚወዘወዝ መሥዋዕት
ለ. መወዝወዝ መሥዋዕቱን በመሥዋዕት አቅራቢው እጅ እና በካህኑ እጅ ማኖርን ያካትታል።እሱም በመሥዋዕት አቅራቢው ለእግዚአብሔር የቀረበውን መሥዋዕት ያሳያል፣ ከዚያም በኋላ ተመልሶ በካህኑ መቀበሉን።
ሐ. ቀኙ ሹሉዳ (ታፋ) መሥዋዕቱን ላከናወነው ካህን ነው
መ. የማንሣት መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ከፍ ይደረግና ተመልሶ ካህኑ ይቀበለዋል

4. የመሥዋዕት አቅራቢው ድርሻ፣ ሌዋ. 7፡15-18

ሀ. የምስጋና መሥዋዕት በሚቀርብበት ቀን ይበላል፣ 7፡15
ለ. ቃል የመግባት (የመሐላ) ወይም የፍቃድ መሥዋዕት በሚቀርብበት ቀን ይበላል ወይም በቀጣዩ ቀን፣ 7፡16
ሐ. ይህ ድርሻ ሁሉ ለእግዚአብሔር የሚሰጥ አልነበረም፣ በእግዚአብሔርም ለካህኑ
መ. እግዚአብሔር በተምሳሌትነት ከመሥዋዕት አቅራቢው እና ከቤተሰቡ እና ከጓደኞቹ ጋር ይሄንን መሥዋዕት ይበላል
ሠ. ይህ መሥዋዕት አጽንዖት የሚሰጠው የኅብረት ግንኙነት መመለሱን ነው

መ. ሌዋውያን 4፡1-5፡13 (6፡24-30) የኃጢአት መሥዋዕት

1. መግቢያ

ሀ. ይህ የመጀመሪያው መሥዋዕት ነው፣ ሥርየት ዋነኛው ነገር ሲሆን።
ለ. ይህ መሥዋዕት ዳግም ያቋቁመዋል፣ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል ያለውን ኪዳን።
ሐ. ይህ መሥዋዕት የሚያካትተው፡

(1) ባለማወቅ የተደረገ ኃጢአት
(2) ሆን ተብሎ ያልተደረገ ኃጢአት
(3) የስሜት ኃጢአት
(4) የግድፈት ኃጢአት
(5) እሱም ሆን ተብሎ የተደረገ ኃጢአትን አያስተሠርይም፣ በትዕቢት ዓመጽ በእግዚአብሔር ላይ የተደረገውን። ሆን ተብሎ ለተደረገ፣ ለትዕቢት፣ ቀደም ብሎ ለታሰበበት ኃጢአት መሥዋዕት አልነበረም (ዘኍ. 15፡27-31)።

2. ፍችው

ሀ. ይህ መሥዋዕት የኃጢአት በደል ቅጣትን ያስተሠርያል።
ለ. ይህም ጸጋን በእግዚአብሔር በኩል እና እምነትን በሰው በኩል ያካትታል።
ሐ. ምንም ዓይነት መሥዋዕት በአምልኮ ሥርዓት መሥዋዕት ምንም አያስገኝም። ከትዕይንቱ ጀርባ ያቅራቢው እምነት ነበር።
መ. ቢሆንም፣ መሥዋዕት ከአቅራቢው መግለጫ ከፍ ያለ ነበር። ለእሱም አንድ ነገር ያደርግለታል። ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት ዳግም ያቋቁምለታል።
ሠ. የአምልኮ ሥርዓት አምላክ የሰጠው የመመለሻ አግባብ ነበር፣ የግል እምነትን የሚተካ ሳይሆን።
ረ. እግዚአብሔር ማንኛውንም ሃይማኖታዊ ድርጊት ይጠላል፣ ከእምነት ጋር እስካልተጎዳኘ ድረስ፣ ኢሳ. 1፡10-20፤ አሞጽ 5፡21-24፤ ሚኪያስ 6፡6-8።

3. የአምልኮ ሥርዓት

ሀ. ለሊቀ ካህኑ፣ ሌዋ. 3-12

(1) ሊቀ ካህን — የተቀባ ካህን

(ሀ) ኃጢአት፣ በስሕተት ሕዝብን መምራት
(ለ) ኃጢአት፣ በሰዋዊ ተፈጥሮው
(ሐ) ሊቀ ካህኑ፣ የማኅበረሰቡ መንፈሳዊ ተወካይ ነው። እሱ ኃጢአትን ከሠራ፣ በእርሱ ምክንያት ሁሉም ኃጢአትን ይሠራሉ። ይህ የአይሁድ የአጠቃሎሽ መረዳት ነው (ኢያሱ 7፤ ሮሜ 5፡12)።

(2) ደንቡ

(ሀ) ሊቀ ካህኑ ነውር የሌለበትን ወይፈን ወደ መሠዊያው ያመጣል
(ለ) እጁንም ራሱ ላይ ይጭናል
(ሐ) ሊቀ ካህኑ እንስሳውን ያርዳል
(መ) ሊቀ ካህኑ በመሸፈኛው ላይ ሰባት ጊዜ ደሙን ይረጫል

i. ይህም መቅደሱን ያነጻል
ii. በተምሳሌትነትም ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን መንገድ ይከፍታል
iii. ደም በዕጣን መሠዊያው ቀንድ ላይ ይደረጋል
iv. ደም ከሚቃጠል መሥዋዕቱ መሠዊያ ላይ እንደፈሰሰ ይቀራል

(ሠ) እሱም ስቡን ሁሉ መሠዊያው ላይ ያደርጋል፣ እንዲቃጠል
(ረ) ቀሪው የእንሰሳው አካል ከሰፈሩ ውጭ ወደ ንጹሕ ስፍራ ይወሰዳል፣ 4፡12፣ እዚያም የመሠዊያው አመድ የሚፈስበት፤ እዚያም ቀሪው የእንስሳው አካል ይቃጠላል

ለ. ለሕዝቡ፣ ሌዋ. 4፡13-21

(1) እነርሱ ኃጢአትን የሚሠሩት የሕግ ትእዛዛት ሲጣሱ ነው፣ 4፡13-21
(2) ደንቡ
(ሀ) ሽማግሌዎች ነውር የሌለበትን ወይፈን ወደ መሠዊያው ያመጣሉ
(ለ) ሽማግሌዎች ራሱ ላይ እጃቸውን ይጭናሉ
(ሐ) ሽማግሌዎች እንስሳውን ያርዳሉ
(መ) ሊቀ ካህኑ ደሙን መሸፈኛው ላይ ሰባት ጊዜ ይረጫል
i. ይህም መቅደቡን ያነጻል
ii. በተምሳሌትነትም ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን መንገድ ይከፍታል
iii. ደም በዕጣን መሠዊያው ቀንድ ላይ ይደረጋል
iv. ቀሪው መሠዊያው መሠረት ላይ ይፈስሳል
(ሠ) ሁሉም የሚቀርበው መሠዊያው ላይ ነው
(ረ)ቀሪው የእንስሳው አካል ከሰፈሩ ውጭ ወደ ንጹሕ ስፍራ ይወሰዳል፣ ቁ. 12፣ እዚያም የመሠዊያው አመድ የሚፈስበት ስፍራ፤ እዚያም ቀሪው የእንስሳው አካል ይቃጠላል
ሐ. ለመሪ፣ ሌዋ. 4፡22-26
(1) መሪ (ገዥ) 4፡22-26
(ሀ) የነገድ መሪ
(ለ) በማኅበረሰቡ ውስጥ ኃላፊነት ያለበት ሰው
(ሐ) ሽማግሌ
(2) ደንቦች
(ሀ) መሪው ወንድ ፍየል ወደ መሠዊያው ያመጣል (የጠና፣ ፀጉራም ፍየል)
(ለ) መሪው እጁን ራሱ ላይ ይጭንበታል
(ሐ) መሪው እንስሳውን ያርደዋል
(መ) ሊቀ ካህኑ በሚቃጠል መሥዋዕቱ መሠዊያ ቀንዶች ላይ ደሙን ያኖራል — ቀሪው ደም በመሥዋዕቱ መሠዊያ ሥር ይፈስሳል
(ሠ) የሰባው ሁሉ መሠዊያው ላይ ይቃጠላል
(ረ) ካህናት ቀሪውን ሥጋ ይበሉታል
መ. ለግለሰብ፣ ሌዋ. 4፡27-35
(1) ለግለሰብ — ኃጢአት ማድረጉን በተረዳ ጊዜ ይሄንን መሥዋዕት እንዲያደርግ ይሆናል
(2) ደንቦች
(ሀ) ግለሰብ ሴት ፍየል ወይም ሴት በግ ያመጣል
(ለ) ግለሰቡ በራሱ ላይ እጁን ይጭናል
(ሐ) ግለሰቡ እንስሳውን ያርዳል
(መ) ካህኑ በመሥዋዕት መሠዊያው ቀንዶች ላይ ደሙን ያኖራል — ቀሪው በመሠዊያው ሥር ይፈስሳል
(ሠ) ስቡ ሁሉ በመሠዊያው ላይ ተደርጎ ይቃጠላል
(ረ) ካህናት ቀሪውን ሥጋ ይበሉታል
ሠ. በኃጢአት መሥዋዕት የሚካተቱ ልዩ ጉዳዮች፣ ሌዋ. 5፡1-13 (እነዚህ ሊሆኑ የሚችሉት ሆን ተብሎ የተደረገ በኪዳን ጓደኛ ላይ የሚፈጸም ኃጢአት ነው)
(1) ምስክር ቀርቦ እማኝነቱን ካልሰጠ (መረጃ የመስጠት እጥረት)፣ 5፡1
(2) የረከሰ እንስሳን መንካት፣ 5፡2
(3) የረከሰ ሰውን መንካት፣ 5፡3
(4) መሐላን በግዴለሽነት መናገር፣ 5፡4
(5) ከላይ ላሉት ኃጢአት መሥዋዕቱ፡
(ሀ) ሴት ፍየል ወይም በግ
(ለ) ሁለት ርግቦች ወይም ሁለት ፔጊኦንስ
(ሐ) መልካም ዱቄት የኤፋህ 1/10ኛ
ረ. የኃጢአት መሥዋዕት የአምልኮ ሥርዓት፣ ሌዋ. 6፡24-30
(1) ካህኑ የቀረውን መብላት ይችላል
(2) ደም ልብሱን ከነካው፣ ልብሱ መታጠብ ይኖርበታል
(3) ደሙ ሸክላውን ከነካው፣ ሸክላው ይሰበራል
(4) ደሙ የነሐስ ዕቃውን ከነካው፣ ዕቃው ይታጠባል
(5) የሚቃጠል መሥዋዕቱ ደም ወደ ቅዱስ ስፍራ ከመጣ፣ ከዚያም ሥጋው መቃጠል ይኖርበታል፣ በካህን አይበላም
ሰ. የኃጢአት መሥዋዕት ጠቀሜታ
(1) ሆን ብሎ ታስቦበት ለተሠራ ኃጢአት ምንም መሥዋዕት አይኖረውም — ሆን ተብሎ ላልሆነ ኃጢአት ወይም ባለማወቅ ለተፈጸመ ኃጢአት ብቻ ነው፣ ሌዋ፣ 4፡15፣18።
(2) ይቅርታ ምንድነው የሚያካትተው፡
(ሀ) በሰው በኩል እምነት
(ለ) በእግዚአብሔር በኩል ምሕረት
ሠ. ሌዋውያን 5፡14-19 የበደል ወይም የመተላለፍ መሥዋዕት
1. መግቢያ

ሀ. የኃጢአት መሥዋዕት ለተፈጸመው ኃጢአት እንደሚሆን፣ የበደል መሥዋዕት ደግሞ በኪዳን ባልንጀራ ላይ በተፈጸመ ጉዳት እና በታሳቢ ማካካሻው ላይ ይሆናል።
ለ. የኃጢአትና የበደል መሥዋዕት እጅግ ተመሳሳይ ናቸው።
ሐ. የግለሰብ መብቶች በአስርቱ ትእዛዛት ላይ ተገልጸዋል (ዘጸአት 20፤ ዘዳግም 5)።
(1) ቤት
(2) የመልካም ነገር ክምችት
(3) ሕይወት
መ. ይህ መሥዋዕት አጽንዖት የሚሰጠው በወንድማችን ላይ ለፈጸምነው ጉዳት ነው፣ ኃጢአት በመሥራት፣ ለደረሰው ጉዳት ስለሚደረገውም ማካካሻና እንዲሁም 1/5 ተጨማሪ።
2. መሥዋዕት የሚሻ ኃጢአት
ሀ. በእግዚአብሔር ላይ እና የእርሱ በሆነ ላይ
(1) በኩራት
(2) በኩር፣ ሌዋ. 5፡14-16
(3) መባ
(4) ያላግባብ የቀረበ መሥዋዕት
(5) ዝቅተኛ ዋጋ ያላቸው ስጦታዎች
ለ. "ሰው ኃጢአት ቢሠራና እግዚአብሔር አትሥሩ ብሎ ካዘዛቸው አንዳቸውንም ቢያደርግ፣ ምንም እንኳ ሳያወቀው ቢሆን፣ በደለኛ ነው፣ እናም ቅጣቱን ይቀበላል።"
ረ. ጥንታዊ መሥዋዕቶች ይቀርቡ የነበረው
1. ከተቆጣ አማልክት ጋር ሰላምን ለማምጣት
2. አማልክትን ለመመገብ
3. ከአማልክት ጋር ለመገናኘት
4. አማልክትን ለማመስገን
5. የይቅርታን ወይም የመታረቅን ስሜት ለማዳበር

**50፡6** ይህ ፈሊጣዊ ማረጋገጫ ነው የያህዌ እንደ ፈጣሪ፣ እና ብሎም ፍርድን ለመስጠት መብት እንዳለው።

▣ **"ሰማያት የእርሱን ጽድቅ ይናገራሉ"** ይህ የሚያረጋግጠው "ተፈጥሯዊ መገለጥን" ነው (መዝ. 8:3፤ 19:1-6፤ 97:6፤ ደግሞም ዮሐንስ 12:7-10 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)።

▣ **"ሴላህ"** መዝ. 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻና መግቢያ ለመዝሙር፣ VII ተመልከት።

**መዝሙር ፡ 50፡7-15**

**7ሕዝቤ፥ ስማኝ፥ ልንገርህ**
**እስራኤልም፥ ስማኝ፥ ልመስክርብህ**
**አምላክስ እኔ አምላክህ ነኝ።**
**8ስለ ቍርባንህ የምዘልፍህ አይደለሁም**
**የሚቃጠል መሥዋዕትህ ሁልጊዜ በፊቴ ነው።**
**9ከቤትህ ፍሪዳን**
**ከመንጋህም አውራ ፍየልን አልወስድም**
**10የምድረ በዳ አራዊት ሁሉ**
**በሺህ ተራራዎች ያሉ እንስሶችም የእኔ ናቸውና።**
**11የሰማይን አዕዋፍ ሁሉ አውቃለሁ፥**
**የምድረ በዳ አራዊትም በእኔ ዘንድ ናቸው።**
**12ብራብም ለአንተ አልነግርህም፥**
**ዓለምና ሞላው የእኔ ነውና።**
**13የፍሪዳውን ሥጋ እበላለሁን?**
**የፍየሉንስ ደም እጠጣለሁን?**
**14ለእግዚአብሔር የምስጋናን መሥዋዕት ሠዋ፥**
**ለልዑልም ስእለትህን ስጥ**
**15በመከራ ቀን ጥራኝ፥**
**አድንህማለሁ አንተም ታከብረኛለህ።**

**50፡7-15** ይህ አንዳ ሦስት አጽንዖቶች አሉት።
1. ቃል ለእርሱ የአምልኮ-ሥርዓት-ተኮር ተከታዮች
2. እርሱ በፍጥረት ላይ ያለው ጌትነት ማስረገጫ፣ እናም የሰው መሥዋዕት የማያስፈልገው መሆኑ፣ በተለይም እነርሱን በመስጠት ሰዎች፣ ያህዌ በእነርሱ እኳያ ሆኖ ለመሥራት ይገደዳል ብለው ማሰብ?

3. የልብ እምነት ስለ ማስፈለጉ (ዘዳ. 10፡16፤ ኤር. 4፡4)፣ የአምልኮ ሥርዓታዊ/አምልኳዊ የመሥዋዕት ሥርዓት ሳይሆን (መዝ. 51፡16-17፤ ኢሳ. 1፡10-15፤ ሆሴ. 6፡6፤ አሞጽ 5፡21-24፤ ሚኪያስ 6፡6-8)

**50፡7** የኪዳን ስብከት ተከታዮች፣ ያህዌ ሲናገር ለመስማት።

1. አድምጥ – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል ተተኳሪ፣ ፈራጁ እየተናገረ ነው*
2. እናገራለሁ – ቢዲቢ 180፣ ኬቢ 210፣ *ፔል ተጓዳኝ*
3. እመሰክርባችኋለሁ – ቢዲቢ 729፣ ኬቢ 795፣ *ሂፊል ተጓዳኝ*

◘ ይህ ቁጥር በርካታ ሐረጎች አሉት፣ ኪዳናዊ ቃላት በመባል የሚታወቁት።

1. ሕዝቤ (ዘጸ. 19፡5-6)
2. እስራኤል ሆይ (ዘዳ. 6፡4-5)
3. አምላክህ፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ (ዘጸ. 20፡2፤ ዘወትር ሌዋውያን ላይ)

የሚያመለክተው ጉዳዩ የሕይወት ስልት የኪዳን ታዛዥነትን ነው፣ እንዲያው መሥዋዕትን ሳይሆን። መሥዋዕት የአምልኮ ሥርዓታዊ መንገድ ነው፣ ቅዱሱ እግዚአብሔር ኃጢአተኛውን የሰው ልጅ ይቅር ለማለቱና በኅብረት ለመቆየቱ። ልብ ዋነኛ ነገር ነው (ዘዳ. 10፡16) እንደ ድርጊቱ እንደ ራሱ!

**50፡10-12** ያህዌ በፍጥረት ሁሉ ላይ ጌትነቱን እያጸና ነው። የ "እያንዳንዱ፣" "እያንዳንዱ ነገር" ተደጋጋሚ አጠቃቀምን ተገንዘብ (ዘዳ. 10፡14፤ ነህ. 9፡6፤ መዝ. 103፡19-22)።

**50፡13** *መሥዋዕት* በብኪ እንደ እግዚአብሔር ምግብ ተደርገው ፈጽሞ አይታዩም ነበር።

1. በሚሶፖታሚያ *ሥነ-መለኮት* ጣዖታት የሰዎችን መሥዋዕት ይመገባሉ።
2. በከነአናውያን *ሥነ-መለኮት*፣ *ሐናዝ ሥጋ* ይበላል ደምም ይጠጣል።

አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ምን ያህሉ የእስራኤል ቃል (*ሥነ-መለኮት* ሳይሆን) በመጀመሪያ የከነአናውያን አፈ-ታሪክ ተጽዕኖ እንዳረፈበት እንዲሁም ኋላ ላይ በይሁዲነት በዞሮአስትሬን *ሥነ-መለኮት*።

**50፡11 "በሜዳ ላይ የሚንቀሳቀስ"** ይህ አወቃቀር (ቢዲቢ 260 I እና ቢዲቢ 961) እዚህጋ ብቻና 80፡14 ላይ ነው የሚገኘው። እሱም ከ "ወፎች" ጋር ትይዩ ነው፣ እና ስለዚህ፣ አንድ ዓይነት ፍጥረት መሆን አለበት (ዘፍ. 1፡24-24)።

1. አነስተኛ እንስሳት (ማለትም፣ የዱር አይጥ፣ አይጥ፣ ቀበሮ፣ ወዘተ)
2. ነፍሳት

እነርሱ ምንም ይሁኑ፣ እነርሱ ያህዌ በዚህ ምድር ላይ ያለው ፍጥረት ሁሉ ባለቤት እንደሆነ የሚያሳዩ ምሳሌ ናቸው (ዝከ. ቁ. 10ሀ)።

**50፡14-15** የዚህ አንጓ የመጨረሻዎቹ ሁለቱ ቁጥሮች ያምልኮ-ሥርዓት-ተኮር ተከታዮች ማድረግ የሚኖርባቸውን ነገሮች ባሕርያት የሚያሳዩ ናቸው፣ እነርሱም ከሌዋውያን 1-7 መሥዋዕት ጋር በቀጥታ የማይዛመዱ።

1. ለእግዚአብሔር የምስጋና መሥዋዕት ሠዋ – ቢዲቢ 256፣ ኬቢ 261፣ *ቃል ተተኳሪ*፤ ይህም የመሐላ መፈጸምን ሊያሳይ ይችላል፣ መዝ. 66፡13-15
2. ስለትህን ለልዑሉ ስጥ – ቢዲቢ 1022፣ ኬቢ 1532፣ *ፔል ተተኳሪ* (ዘኍልቍ 30፤ ዘዳ. 23፡21፤ መዝ. 22፡25፤ 56፡12፤ 61፡8፤ 65፡1፤ 71፡11)
3. እኔን ጥራኝ (ማለትም፣ ጸሎት) በችግር ጊዜ – ቢዲቢ 894፣ ኬቢ1128፣ *ቃል ተተኳሪ*

እነርሱ እነዚህን ነገሮች ካደረጉ፣ እንግዲያውስ ያህወ "ያድናቸዋል" (ማለትም፣ "ይታደጋቸዋል፣" ቢዲቢ 322፣ ኬቢ 321፣ *ፔል ያልተጠናቀቀ*) እያንዳንዱን። በምላሹም እያንዳንዱ እግዚአብሔርን "ያከብራል" (ቢዲቢ 457፣ ኬቢ 455፣ *ፔል ያልተጠናቀቀ*)።

## *መዝሙር* ፡ 50፡16-21

**16ኃጢአተኛውን ግን እግዚአብሔር አለው።**
**ለምን አንተ ሕጌን ትናገራለህ?**
**ኪዳኔንም በአፍህ ለምን ትወስዳለህ?**
**17አንተስ ተግሣጼን ጠላህ፥**
**ቃሎቼንም ወደ ኋላህ ጣልህ።**
**18ሌባውን ባየህ ጊዜ ከእርሱ ጋር ትሮጥ ነበር**
**እድል ፈንታህንም ከአመንዝሮች ጋር አደረግህ።**
**19አፍህ ክፋትን አበዛ፥**
**አንደበትህም ሽንገላን ተበተበ።**
**20ተቀምጠህ ወንድምህን አማኸው፥**
**ለእናትህም ልጅ ዕንቅፋት አኖርህ።**
**21ይህን አድርገህ ዝም አልሁህ**
**እኔ እንደ አንተ እሆን ዘንድ ጠረጠርህ**
**እዘልፍሃለሁ በፊትህም እቆማለሁ።**

**50፡16-21** ይህ አንጓ ለእምነተ-ቢስ ተከታይ የተመለከተ ነው፣ እዚህ "ኃጢአተኛ" ተብሏል (ቢዲቢ 957)። እነዚህ ወንዶች/ሴቶች/ወጣቶች የኪዳኑ ሕዝቦች ናቸው፣ እነርሱም በቃላቸው፣ በድርጊታቸው፣ እና በቸልተኝነታቸው፣ ዓመጸኝነታቸውን፣ ራስ ወዳድነታቸውን ያሳዩ (ማለትም፣ ከአስርቱ ትእዛዛት ሦስቱን የተላለፉ)።

1. እነርሱ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ኪዳኑ ይናገራሉ፣ ነገር ግን ችላ ይሉታል፣ ቁ. 16 (ማለትም፣ የኪዳን ቁጥሮችን ወይም የአምልኮ ሥርዓትን መደጋገም፣ ያለ እምነትና የሕይወት ስልት)
2. እነርሱም መስፈርቶቹን ይጠላሉ፣ ችላ ይሏቸዋልም (ማለትም፣ "ቃሌን ወደ ኋላቸው ይጥላሉ"፤ እነርሱ ተግባራዊ አምላክ-የለሽ ናቸው)፣ ቁ. 17፤ ነህ. 9፡26
3. በክፉ አድራጎት ቅር የማይሰኙ ብቻ አይደሉም፣ እንደዚያ ከሚያደርጉ ጋርም ይተባበራሉ እንጂ፣ ቁ. 18 ("በፍሬአቸው…፣" ማቴ. 7:16-20፤ 1 ቆሮ. 15:33)
4. ቃላቸው ልባቸውን ይገልጣል፣ ቁ. 19-20 (ማቴ. 12:33-37)
5. ያያህዌን ትዕግሥት ከእነርሱ ጋር ለመሆኑ እንደ ማረጋገጫ ይወስዱታል (መክ. 8:11፤ ኢሳ. 57:11)

ያህዌ ግን ይሠራል።
1. እመረምርሃለሁ – ቢዲቢ 406፣ ኬቢ 410፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ነገሩን በፊትህ በሥርዓት አኖራለሁ – ቢዲቢ 789፣ ኬቢ 884፣ *ቃል* ተጓዳኝ፣ ማለትም፣ ሕጋዊ አገባብን አዘጋጃለሁ፣ ኢዮብ 13:18፤ 23:4፤ 32:14፤ 33:5

**50:18**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ከእርሱ ጋር ተደሰትክ"** |
| **አኪጀት** | **"ከእርሱ ጋር ተራመድክ"** |
| **አየተመት፣ አእቅ፣** | |
| **አኢመቅ** | **"ወዳጅነት አበጀህ"** |
| **LXX** | **"እሱን ተደባለቅኸው"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"ከእርሱ ጋር ተወዳጀህ"** |
| **የተእመቅ** | **"በባልንጀርነት መረጥከው"** |

ኤምቲ "ተደሰትክ" የሚል አለው (ቢዲቢ 953፣ ኬቢ 1280፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ ከ*ዋው ጋር*)። LXX፣ ሶርያኛ፣ እና ቫልጌት "ሮጥክ" ወይም "ተባበርክ፣" የሚል አላቸው፣ እሱም ከትይዩው ጋር በተሻለ የሚገጥም። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ለኤምቲ ቃላት አመሠራረት "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ)።

**50:19**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አየተመት** | **"በሜዳ የሚንቀሳቀሰው ሁሉ"** |
| **አኪጀት** | **"በሜዳ ያሉ የዱር እንስሳት"** |
| **አእቅ** | **"በሜዳ ያሉ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ሁሉ"** |
| **አኢመቅ** | **"በሜዳ የሚንቀሳቀሰው ሁሉ"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"በሜዳ ያሉ ፍጥረታት"** |
| **የተእመቅ** | **"በሜዳ ያሉ ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት"** |

ኤምቲ "በሜዳ ያሉ ተንቀሳቃሽ ፍጥረታት" የሚል አለው (ቢዲቢ 265 I አወቃቀር ቢዲቢ 961)። የመጀመሪያው ቃል እዚህጋ ብቻ እና መዝ. 80፡13 ላይ ነው ጥቅም ላይ የዋለው። እሱም የሚጠቅሰው "ሕይወት ባላቸው ነገሮች የተሞላን" ነው፣ የዘፍ. 1፡24-26።

**50፡21 "እኔ እንደ አንተ እሆን ዘንድ አሰብክ"** ይህ ሐረግ በ "መሆን" ግሥ ተጠናክሯል፣ በሁለቱም ባልተወሰነ አወቃቀር እና ያልተጠናቀቀ ግሥ።

ወጣ ያሉ አማኞች ዘወትር የሚገምቱት ደጎነታቸው እንደተጠበቀና እምነታቸው እንደ እግዚአብሔር እንደሆነ ነው። ራዕይ የመጨረሻው ዳኛ ነው! የወደቁ ሰዎች፣ የኪዳኑ ሰዎች ቢሆኑም፣ እግዚአብሔርን ወይም ቃሉን ሊረዱ አይችሉም፣ ነገር ግን እንደተረዱት ያስባሉ! ለእኔ እንደ መጽሐፍ ቅዱስ መምህር፣ ማቅረብ ያለብኝ ዋነኛ ነገር ለመማር የሚቻል፣ ንስሐ የሚገባ፣ ትሑት መንፈስ ነው። የእኔ ሥነ-መለኮት የእግዚአብሔር ሥነ-መለኮት አይደለም። እሱ የእኔ ወግ ክፍል አይደለም። ማስታወስ የሚኖርብኝ ሰዎች ሁሉ
1. ከታሪካዊ ሁኔታ ውስጥ
2. ኃጢአተኛ፣ የተጎዱ ሰዎች
3. ለቀኖናዊነትና ለትዕቢት በቀላሉ የሚሳቡ መሆናቸውን ነው

የበለጠ ባወቅህ ቁጥር፣ ምንም አለማወቅህን የበለጠ ታውቃለህ!

## መዝሙር ፡ 50፡22-23

**[22]እግዚአብሔርን የምትረሱ እናንተ፥ ይህን አስተውሉ**
**አለዚያ ግን ይነጥቃል የሚያድንም የለም።**
**[23]ምስጋና የሚሠዋ ያከብረኛል**
**የእግዚአብሔርን ማዳን ለእርሱ የማሳይበት**
**መንገድ ከዚያ አለ።**

**50፡22-23** ይህ የማጠቃለያ መግለጫ ነው፣ ለሁለቱም መልእክት ያለው፣ ለአምልኮ-ሥርዓት-ተኮር ተከታዮች (በአንድምታ) እና ለእምነት-ቢስ ተከታዮች (በቀጥታ የሚመለከታቸው)። ሁለቱም "ሊገነዘቡት" ይገባል (ቢዲቢ 106፣ ኬቢ 122፣ *ቃል* ተተኳሪ)።
1. ለክፉዎች
   ሀ. እግዚአብሔርን የሚረሱ፣ ቁ. 22ሀ
   ለ. ፍርድ ይመጣል፣ ማንም መዳን አይችልም፣ ቁ. 22ለ
2. ለታማኝ በተቃርኖ
   ሀ. የምስጋና መሥዋዕት ለሚሠዋ፣ ቁ. 23ሀ (ዝከ. ቁ. 14ሀ)

ለ. እኔን የሚያከብር፣ ቁ. 23ሀ (ዝኪ. ቁ. 15ለ)
ሐ. በቀና መንገድ የሚሄድ
ያህዌ ክፉን ያጠፋል (ቁ. 22ለ)፣ ታማኞችን ግን ያድናል (ቁ. 23ሐ)።

**50፡22ለ "አለበለዚያ እንዳልሰባብርህ"** ይህ የያህዌ ምናባዊ ምስያ ነው፣ እንደ አንበሳ (መዝ. 7:2፤ 17:12፤ ሆሴ. 5:14፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አንበሶች በብኪ መዝ. 7:2 ላይ)። እጅግ የከፋ መዘዝ አለው፣ ዓመጻና ቀጣይነት ያለው አለማመን! ፍትሕ ያለ ውጤት አይሆንም!

▣ **"የሚታደግም የለም"** እግዚአብሔር ከተቃወመን፣ ማን ሊረዳን ይችላል?! እሱ እና እሱ ብቻ ነው የሚታደግ። ተመሳሳይ ጽንሰ-ሐሳብ በአዎንታዊነት ሮሜ 8፡31-39 ላይ ተገልጿል።

**50፡23ለ** ይህ አሻሚ የቅኔ ስንኝ ነው። በጥሬው "መንገድ ማሳያ" ማለት ነው። ግሡ (ቢዲቢ 962፣ ኬቢ 1321) ሰፊ የፍች መስክ አለው። አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች እሱን የሚወስዱት እንደ ጻድቅ፣ ኪዳናዊ፣ ታዛዥ የሕይወት ስልት ጠቃሽ አድርገው ነው። እሱም በርግጥ ሊወሰድ ይችላል፣ ተገቢ መሥዋዕትን እንደሚያመለክት!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ለመዝሙሩ እንዴት ያለ ርዕስ ትሰይምለታለህ?
2. እንዴት ያሉ ሁለት የኪዳን ሕዝቦች ነው የተገለጹት? (ቁ. 7-15፣ 16-21)
3. በፍርድ ላይ ያለው ማነው?
4. መሥዋዕት ስሕተት ነውን?
5. "እግዚአብሔር ዝም አለ" ምን ማለት ነው? እግዚአብሔር ለምን ዝም ይላል? (ቁ. 21)

## መዝሙር 51
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ያዘነ ኃጢአተኛ ጸሎት ለይቅርታ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር፣ ነቢዩ ናታን ወደ እርሱ በመጣ ጊዜ፣ ወደ ቤርሳቤህ ከደረሰ በኋላ። | የንስሐ ጸሎት | የፈውስና የሞራል መታደስ ጸሎት | የይቅርታ ጸሎት | የመጸጸት ጸሎት |
| 51:1-4 | | | | |
| | 51:1-2 | 51:1-2 | 51:1-2 | 51:1-2 |
| | 51:3-4 | 51:3-5 | 51:3-5 | 51:3-4ለ |
| | | | | 51:4c-5 |
| 51:5-9 | | | | |
| | 51:5-6 | | | |
| | | 51:6-9 | 51:6-9 | 51:6-7 |
| | 51:7-9 | | | |
| | | | | 51:8-9 |
| 51:10-13 | | | | |
| | 51:10-11 | 51:10-12 | 51:10-13 | 51:10-11 |
| | 51:12-13 | | | 51:12-13 |
| | | 51:13-14 | | |
| 51:14-17 | | | | |
| | 51:14-17 | | 51:14-15 | 51:14-15 |
| | | 51:15-17 | | |
| | | | 51:16-17 | 51:16-17 |
| 51:18-19 | | | | |
| | 51:18-19 | 51:18-19 | 51:18-19 | 51:18-19 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ ከንስሐ መዝሙሮች አንዱ ነው፣ መዝሙር 6፤ 32፤ 38፤ 51፤ 102፤ 130፤ እና 143። መዝሙር 51 ከመዝሙር 32 ጋር ሊዛመድ ይችላል፣ ማለትም፣ የዳዊት ኃጢአት ሊሆን ይችላል፤ መዝሙር 32 ኋላ ላይ የተጻፈ ሊሆን ይችላል፣ በዳዊት ሕይወት።

ለ. ምንም እንኳ የመዝሙር 51 መግቢያ በኤምቲ የኋላ ጭማሪ ቢሆንም፣ እሱ የዚህን መዝሙር ርዕሰ-ጉዳይ በትክክል ሊያንጸባርቅ ይችላል። ለዳራው የተሟላ መረዳት፣ 2 ሳሙኤል 11 እና 12ን አንብብ።

ሐ. ዳዊት፣ እንደ እስራኤል ንጉሥ፣ የእግዚአብሔር ይፋዊ ተወካይ ነበር፣ በሕዝቡ መካከል። እሱ ይሄንን የተቀደሰ እምነት ካደ። እሱ እግዚአብሔርን "ያህዌ" ብሎ አልጠራም፣ በዚህ መዝሙር (ይህ ግን የመጽሐፍ II ባሕርይ ነው፣ በመዝሙራት)። ሆኖም፣ እሱ የእግዚአብሔርን የማይለወጥ ባሕርይ ፍቅሩንና ምሕረቱን ጠራ (ሚል. 3፡6) ራሱን እንደጣለ፣ ያለ ማሳበብ፣ በእግዚአብሔር እጅ።
ምንም ዓይነት የብኪ መሥዋዕት አልነበረም፣ ሆን ተብሎ፣ ቀድሞ ለታሰበበት ኃጢአት (ሌዋ. 4፡2፤ 22፤ 27፤ 5፡15-18፤ 22፡14)።

1. በሌላይቱ ሚስት ላይ መሴሰን
2. ዝሙት እንድትፈጽም ማስገደድ
3. የንጉሥ ሠራዊት ለሆነው ባሏ መዋሸት
4. በሌሎች በኩል (ማለትም፣ የእስራኤልን ወታደሮች በማጭበርበር) እሱን መግደል
5. አጠቃላዩን ነገር ለመሸፋፈን መሞከር፣ ንስሐ ከመግባት ይልቅ

መ. "ይቅርታ"ን ለመግለጽ ምን ያህል የተለያዩ መግለጫዎች ጥቅም ላይ እንደዋሉ ተገንዘብ።

1. መሸፈን — ቁ. 1፣ 9
2. ማጠብ — ቁ. 2፣9
3. ማጽዳት — ቁ. 2
4. ማንጻት — ቁ. 7
5. ፊትህን ሸፈንከ — ቁ. 9
6. መታደግ — ቁ. 14

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 51፡1-4**

**1አቤቱ፥ እንደ ቸርነትህ መጠን ማረኝ**
**እንደ ምሕረትህም ብዛት መተላለፌን ደምስስ።**
**2ከበደሌ ፈጽሞ እጠበኝ፥**
**ከኃጢአቴም አንጻኝ**
**3እኔ መተላለፌን አውቃለሁና፥**
**ኃጢአቴም ሁልጊዜ በፊቴ ነውና።**
**4አንተን ብቻ በደልሁ፥**
**በፊትህም ክፋትን አደረግሁ፥**
**በነገርህም ትጸድቅ ዘንድ**
**በፍርድህም ንጹሕ ትሆን ዘንድ።**

**51፡1-2** የዚህን አንጓ ጽሑፋዊ ፍሰት ተገንዘብ፣ እሱም የአማኙን የታወቀ ኃጢአት ንስሐ የያዘ። አራት (አምስት የሚሆኑ፣ ቁሬ) ተተኳሪ ጥያቄዎች አሉ።

1. ቸርነትህ በእኔ ላይ ይሁን – ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334፣ ቃል ተተኳሪ፤ ይህ ተደጋጋሚ የጸሎት ጥያቄ ነው (መዝ. 4፡1፤ 6፡2፤ 9፡13፤ 25፡16፤ 26፡11፤ 27፡7፤ 30፡10፤ 31፡9፤ 41፡4፣10፤ 56፡1፤ 57፡1 [ሁለቴ] ወዘተ.) ለቸሩ እግዚአብሔር (ቢዲቢ 337፣ cf. መዝ. 86፡15፤ 103፡8፤ 111፡4፤ 116፡5፤ 145፡8፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9፡10ለ ላይ)
   ሀ. እንደ ምሕረትህም ብዛት (ቢዲቢ 338፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7)
   ለ. እንደ ርኅራኄህ ታላቅነት ብዛት (ማለትም፣ አወቃቀር ቢዲቢ 913 እና ቢዲቢ 933፣ መዝ. 25፡6፤ 69፡16፤ 119፡156፤ 145፡9)
2. መተላለፌን ደምስስ – ቢዲቢ 562፣ ኬቢ 567፣ ቃል ተተኳሪ፣ ዝከ. ቁ. 9፣ ይህ ቃል ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ኃጢአተኞችን ለመደምሰስ ነው (መዝ. 9፡5፤ 69፡28፤ 109፡13) ከሕይወትና ከሕይወት መጽሐፍ (ዘጸ. 32፡32-33፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9፡5 ላይ)
   ይህ የይቅርታና ወደ መለኮት ኅብረት የመመለስ "ልምምድ" ጽንሰ-ሐሳብ ደግሞ አኪ ላይ ይገኛል፣ በተለይም ዕብ. 9፡14፤ 1 ዮሐንስ 1፡7፣9።
   ሦስቱም ተመሳሳይ የ"ኃጢአት" ስሞች ደግሞ ዘጸ. 34፡7 ላይ ይገኛሉ። በአስገራሚነቱ "ደምስስ" የሚለው ግሥ ዘጸአት 32፡ 32-33 ላይ ይገኛል። መዝሙረኛው የዘጸአት መጽሐፍን ግምት ውስጥ አስገብቶ ሊሆን ይችላል።
   ግሡ ደግሞ ኢሳ. 43፡25፤ 44፡22 ላይ ይገኛል። እሱም ታላቁን እውነት ያስረግጣል፣ ይኸውም እግዚአብሔር ምሕረትን ሲያደርግ፣ እግዚአብሔር መርሳቱን ያስረግጣል፣ — ኢሳ. 1፡18፤ 38፡17፤ 43፡25፤ 44፡22፤ ሚኪያስ 7፡19 ላይ ማስታወሻ ተመልከት። በርካታ የተለያዩ ዘይቤዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፣ ሁሉም ግን የሚሉት "ከእይታ ውጭ፣ ከአእምሮ ውጭ" ነው።
   በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ቀለም አሲድ ነበር። አንዱ ፓፒረስ ገጽ (ወረቀት) ላይ ሲጽፍ ቀለሙ ወደ ዕቃው ውስጥ ይገባና ሊጠፋ አይችልም ነበር። አንድን ነገር ማጥፋት የእግዚአብሔር ተአምር ነው፣ ልክ በቀለም የተነከረ ልብስን ነጭ እስከሚሆን ማጠብ (ኢሳ. 1፡18) እንደማይቻል (ማለትም፣ የሚያነጻ አልነበረም)። ይቅርታ የእግዚአብሔር ተአምር ነው!
3. እጠበኝ – ቢዲቢ 460፣ ኬቢ 459፣ ፒል ተተኳሪ፣ እዚህጋ መዝሙር ላይ እና ፒል ያልተጠናቀቀ መዝ. 51፡7ላይ፤ በብዛት ሌዋውያን ላይ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ለአምልኮ የማንጻት ሥርዓት
4. "ፈጽሞ" (ኤምቲ ሂፊል ያልተጠናቀቀ ፍጹም አለው፣ ነገር ግን ማሶረቲካዊ የአይሁድ ሊቃውንት የሚሉት ለውጡ ወደ ሌላ ተተኳሪ ነው) – ቢዲቢ 915፣ ኬቢ 1176፣ ሂፊል ተተኳሪ
5. አንጻኝ – ቢዲቢ 372፣ ኬቢ 369፣ ፒል ተተኳሪ፣ መዝሙር ላይ እዚህጋ ብቻ፣ እና ቃል ያልተጠናቀቀ 51፡7 ላይ፤ በዋነኛነትም ሌዋውያን ላይ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ንጹሕ የሆነ ነገርን ለማስታወቅ።

**51፡1 *"መተላለፍ"*** በርካታ ቃላት አሉ የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ላይ ለማመጹ፣ በዚህ አንጓ ላይ የሚገኙ።

1. *መተላለፍ*፣ 51፡1፣3 – ቢዲቢ 833፤ ኢሳ. 59፡12-13፤ አሞጽ 5፡12፤ ሚኪያስ 1፡5 (ሁለቴ)፣13፤ የእርሱ *መሠረታዊ ፍችም* በእግዚአብሔር ላይ *ማመጽ* ነው
2. በደል፣ ቁ. 2፣5፣9 – ቢዲቢ 730፣ መዝ. 32፡5 (ሦስቴ)፣ ኢሳይያስ፣ ኤርምያስ፣ እና ሕዝቅኤል ላይ ተዘውትሮ ጥቅም ይ የዋለ፣
3. *ኃጢአት*፣ ቁ. . 2፣9፣13 – ቢዲቢ 308፣ መዝ. 32፡5 (ሁለቴ)፣ የእርሱ *መሠረታዊ ፍች "መሳት"* ነው፤ *መሠረታዊ ሥሩ* ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው "ለኃጢአት *መሥዋዕት*" ነው
4. ክፉ፣ ቁ. 4 – ቢዲቢ 948 II፣ እጅግ የተለመደ ቃል፣ መዝ. 5፡4፤ 7፡4፣9፤ 10፡6፣15፤ 23፡4፤ 34፡13፣14፣16፤ 36፡4፤ 37፡27፤ 41፡5፤ 49፡5፤ 52፡3፤ 54፡5፣ *ወዘተ*።

አንዱ ሊናገር ይችላል፣ ጽንሰ-ሐሳቡ የቱን ያህል ጠቃሚ እንደሆነ፣ ለባህል/ቋንቋ፣ በምን ያህል ቃላት ለመግባባት ወይም ጽንሰ ሐሳቡን ለማብራራት ጥቅም ላይ መዋሉን። ዕብራይስጥ በርካታ ቃላት አሉት፣ በእግዚአብሔር ላይ ኃጢአት ለመሥራት/ለማመጽ።

▣ ***"ኃጢአት"*** ይህ አንስታይ ጾታ ስም (ቢዲቢ 308) የሚገኘው 51፡ 2፣3፣9፣13 ላይ ነው። ተባዕታይ ጾታ ስም (ቢዲቢ 307) 51፡5፣9 ላይ ነው። ግሡ (ቢዲቢ 306፣ ኬቢ 305) 51፡4፣7 ላይ ነው።

**51፡3-4** እነዚህ ቁጥሮች የሚገልጡት የኃጢአትን ውስጣዊ መዘዝና ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖረውን ኅብረት አስፈሪ መቋረጥ ነው።

1. *"መተላለፌን አውቃለሁና"* — *ያለማወቅ ኃጢአት አይደለም፣ ግልጽ የሆነ ዓመጸኝነት እንጂ*።
2. *"ኃጢአቴ ሁልጊዜ በፊቴ ነውና"* — በደል ሊለዝብ ወይም ሊቀናነስ አይችልም። እሱ ቋሚ የሆነ አስታዋሽ ነው፣ የተሰበረውን ኅብረትና የእርሱም ውጤቶች።
3. *"አንተን፣ አንተን ብቻ በደልሁ"* — ይህ *ሥነ-መለኮታዊ* መግለጫ ነው (ዘፍ. 20፡6፤ 2 ሳሙ. 12፡13፤ መዝ. 41፡4)። ኃጢአት የሚታወቀው የሰው *ሥራ* ከመለኮታዊ ትእዛዝ ትይዩ ሲቀመጥ ነው (ሮሜ. 3፡20፣25፤ 4፡15፤ 5፡13፣20፤ ሐዋ. 17፡30)።

   ይህ የተጎጂዎችን *ሥቃይ* ለማንኳሰስ አይደለም፣ ነገር ግን ባጠቃላይ ኃጢአት ሁሉ በአንዱና ብቸኛው ቅዱስ አምላክ ላይ የተደረገ መሆኑን ለማስገንዘብ ነው!

**51፡4ሐ-መ** አእቅ የእነዚህን ሁለት የቅኔ ስንኞች ፍቺ ይዟል።

"ስለዚህ በእኔ ላይ መፍረድህ ልክ ነህ፤ እኔን በመኮነንህ ጻድቅ ነህ።"

ይህም በጳውሎስ ተጠቅሷል፣ ከLXX ሮሜ 3፡4 ላይ። እሱም የተገለጸው "ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ከሆነ እግዚአብሔር እውነተኛ ይሁን" በሚል ነው።

***መዝሙር ፡ 51፡5-9***

**[5]እነሆ፥ በዓመፃ ተፀነስሁ፥**
**እናቴም በኃጢአት ወለደችኝ።**
**[6]እነሆ፥ እውነትን ወደድህ**
**የማይታይ ስውር ጥበብን አስታወቅኸኝ።**
**[7]በሂሶጵ እርጨኝ፥ እነጻማለሁ እጠበኝ፥**
**ከበረዶም ይልቅ ነጭ እሆናለሁ።**
**[8]ሐሤትንና ደስታን አሰማኝ፥**
**የሰበርሃቸውም አጥንቶቼ ደስ ይላቸዋል።**
**[9]ከኃጢአቴ ፊትህን መልስ፥**
**በደሌንም ሁሉ ደምስስልኝ።**

**51፡5** ይህ ቁጥር ከቁጥር 1-4 ጋር ሊሄድ ይችላል። እሱም ማሳበቢያ አይደለም፣ ነገር ግን አስፈሪ እውነታ ነው፣ የወደቀው ሰው ሁኔታ (ዘፍ. 8፡21፤ 1 ነገ. 8፡46፤ ኢዮብ 14፡1-4፤ 15፡14፤ 25፡4፤ መዝ. 58፡3፤ ምሳ. 20፡9፤ ኢሳ. 48፡8፤ ሮሜ. 3፡9-18፣23፤ ኤፌ. 2፡3፤ ሁሉም የሚገልጹት የወደቀውን የሰው ልጅ ሁኔታ ነው፣ የዘፍጥረት 3። ርግጥ ነው አብዛኞቹ ራቢዎች አጽንዖት የሚሰጡት የኃጢአት መነሻ ዘፍጥረት 6 እንደሆነ ነው። ሐዋርያው ጳውሎስ የአኪ ደራሲ ነው፣ እሱም በዘፍጥረት 3 ላይ የሚያተኩር፣ እንደ ኃጢአት ምንጭና መዘዙ)።

ለእኔ *ሥነ-መለኮታዊው* ጉዳይ የልጆች ኃጢአተኝነት ነው፣ ከሞራል ኃላፊነት ዘመን በፊት። ካልቪኒዝም አጽንዖት የሚሰጠው የሰው ልጅ አጠቃላይ የሞራል ውድቀት ነው፣ በሁሉም ስፍራ፣ ከልደት እስከ ሞት። እኔ ባመዠኙ የምሳበው ወደ መረዳት የሰው ዓመጸኝነት ጽንሰ-ሐሳብ ነው። ይህም ማለት ልጅ እስከሚያውቅ ድረስ፣ እሱ/እሷ የእግዚአብሔርን ሕግጋት ለመጣስ፣ እነርሱ አላመጹም! ኃጢአት ግልጽ የሆነ እይታ ያለው ዓመጸኝነትን ያካትታል! እኛ በአዳም/ሔዋን ኃጢአተኞች ነን (ሮሜ 5፡12-21) እና ደግሞ ኃጢአትን ለማድረግ መርጠናል። ሁለቱም እውነት ነው!

**51፡6-9** *መዝሙረኛው* እግዚአብሔርን ይጠይቃል ወደ ቀድሞው ስፍራ/አቋም ኅብረት እንዲመልሰው። ኃጢአት *መሥራቱን* ተቀብሏል (51፡3-4) እናም ይቅርታን ጠይቋል (51፡1-2)። ይህ አንጓም እነዚህን ይደግማል።

1. *ኃጢአት መሥራቱን መቀበሉን*
   - *ሀ. ቁ.* 5
   - *ለ. ሁለት ተተኳሪዎች*
     1. (1) *"ፊትህን ከኃጢአቴ መልስ"* – ቢዲቢ 711፣ ኬቢ 771፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
     2. (2) *"መተላለፌን ደምስስ"* – እንደ ቁ. 1 ተመሳሳይ ("የእግዚአብሔር መጽሐፍ" ደግሞ መዝ. 139፡16 ላይ ተጠቅሷል፣ ከታች "ምሥጢር" የሚለውን ማስታወሻ ተመልከት)

2. ይቅርታን ፈልጓል
   ሀ. እግዚአብሔር ይፈልጋል "እውነትን ከውስጠኛው ሕላዌ" (ቢዲቢ 711፣ "ምሥጢር" የሚለውን አጠቃቀም ማስታወሻ እይ [ቢዲቢ 712] መዝ. 139፡15 ላይ)
   ለ. እግዚአብሔር እውነቱ እንዲታወቅ ማድረጉ ያስደስታል
   ሐ. የጸሎት ጥያቄዎች (6 ያልተጠናቀቁ)
      (1) አንጻኝ – ቢዲቢ 306፣ ኬቢ 305፣ ፒኤል ያልተጠናቀቀ
      (2) ንጹሕ እሆናለሁ – ቢዲቢ 372፣ ኬቢ 369፣ ቃል ያልተጠናቀቀ (ማለትም፣ የመንጻት ውጤት)
      (3) እጠበኝ – ቢዲቢ 460፣ ኬቢ 459፣ ፒኤል ያልተጠናቀቀ
      (4) ከበረዶ ነጭ እሆናለሁ – ቢዲቢ 526፣ ኬቢ 517፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ(ማለትም፣ የመታጠብ ውጤት ኢሳ. 1:18)
      (5) ደስታን አሰማኝ (ቢዲቢ 965) እና ሐሴትን (ቢዲቢ 970) – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ
      (6) አጥንቶቼ … ይደሰቱ – ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189፣ ቃል ያልተጠናቀቀ ("የተሰበሩ አጥንቶች" የብኪ ፈሊጥ ነው፣ ለመለኮታዊ ፍርድ፣ ኢሳ. 38:13፤ ሰቆ. 3:4)

መዝሙረኛው በጥልቀት ፈልጓል፣ ከእግዚአብሔር ጋር የሚያውቀው የቀረበ ወዳጅነት፣ ይኸውም በእርሱ ኃጢአት ምክንያት የተጎዳው፣ በእግዚአብሔር ጸጋና ምሕረት ሊመለስ እንደሚችል።

**51፡6 "ይሻል"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 342፣ ኬቢ 339፣ ቃል የተጠናቀቀ) ቁጥር 6 ላይ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ማለትም እግዚአብሔር "መፈለጉን" (ማለትም፣ እውነትን በውስጠኛው ሕላዌ) እና 51፡16 ላይ የማይፈልገውም (ቃል ያልተጠናቀቀ፣ ማለትም፣ ያልታሰበበት መሥዋዕት ወይም ሆን ተብሎ ለተሠራ ኃጢአት የሆነ መሥዋዕት)።

**51፡7 "ሂሶጵ"** አነስተኛ የበረሀ ዕጽ (ቢዲቢ 23) አንድ ላይ ተደርጎ ፈሳሽን ለመርጨት ጥቅም ላይ ይውል ነበር፣ ለአምልኮ ሥርዓት ክብረ በዓላት።
1. የፋሲካ ጠቦት በቤቶች መቃን ላይ – ዘጸ. 12፤21-22
2. ለምጻምን በማንጻት ሥነ ሥርዓት ላይ – ሌዋ. 14:4፣6 (ለለምጻም ቤቶች፣ ሌዋ. 14:19፣51፣52)
3. ቀይ ጊደርን ከማቃጠል የአምልኮ ሥርዓት ጋር በተያያዘ (ማለትም፣ የመንጻት አመድ) – ዘኁ. 19:6፣18
4. ሙሴ የሕግ መጽሐፍን ከመርጨቱ ጋር በተያያዘ – ዕብ. 9:19፣ ዘጸ. 24:6-8

**መዝሙር ፡ 51፡10-13**

**10አቤቱ፥ ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ፥**
**የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ።**
**11ከፊትህ አትጣለኝ፥**
**ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድብኝ።**
**12የማዳንህን ደስታ ስጠኝ፥**
**በእሽታ መንፈስም ደግፈኝ።**
**13ለሕግ ተላላፎች መንገድህን አስተምራለሁ፥**
**ኃጢአተኞችም ወደ አንተ ይመለሳሉ።**

**51፡10-13** ይህ አንጓ ደግሞ በርካታ የጸሎት ጥያቄዎች አሉት (ተተኳሪዎች፣ ተጽዕኖዎች)፣ እነርሱም የግል እምነት መታደስን የሚጠቅሱ። ይህም ሊመጣ የሚችለው በሉዓላዊው አምላክ ሥራ ነው፣ መዝሙረኛው ግን ራሱን ማቅረብ ይኖርበታል፣ እንዲደረግለት።
1. ንጹሕ ልብን ፍጠርልኝ – ቢዲቢ 135፣ ኬቢ 153፣ ቃል ተተኳሪ፣ ሕዝ. 36:26-27፤ እሱ ተአምራትን ወይም መታደስን ሽቷል (ባራ ጥቅም ላይ የሚውለው ለእግዚአብሔር ብቻ ነው፣ ዘፍ. 1:1)
2. የቀናውንም መንፈስ በውስጤ አድስ – ቢዲቢ 293፣ ኬቢ 293፣ ፒኤል ተተኳሪ፣ መዝ. 78:37
3. ከፊትህ አትጣለኝ – ቢዲቢ 1020፣ ኬቢ 1527፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ 2 ነገ. 13:23 እና በአሉታዊ 2 ነገ. 24:20፤ ኤር. 7:15
4. ቅዱስ መንፈስህንም ከእኔ ላይ አትውሰድ – ቢዲቢ 542፣ ኬቢ 534፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ኢሳ. 63:10፣11፤ ሕዝ. 36:26-27
5. የማዳንህን ደስታ ስጠኝ – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ ሂፊል ተተኳሪ
6. በእሽታ መንፈስ ተቀበለኝ – ቢዲቢ 701፣ ኬቢ 759፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ከቁ. 3፣4 ጋር ለመግጠም

በውስጣዊ፣ ግላዊ የእምነት ገጽታ ላይ ያለውን አጽንዖት ተገንዘብ (ማለትም፣ ኢሳ. 26፡9)። የዚህ መንፈሳዊ መታደስ ውጤት የሚሆነው
1. ለሕግ ተላላፎች መንገድህን አስተምራለሁ — ቢዲቢ 540፣ ኬቢ 531፣ ፒኤል ተጓዳኝ፤ ኅብረትና እግዚአብሔርን ማወቅ ቀድሞ መምጣት እንዳለበት ተገንዘብ፣ ዕዝራ 7፡10
2. ኃጢአተኞች ይለወጣሉ ("ወደ ኋላ ይመለሳሉ") — ተመሳሳይ ግሥ እንደ 51፡12ሀ፣ "ለመመለስ፣" ግን ቃል ያልተጠናቀቀ

**51፡10 "ልብ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 4፡7 ላይ። የሰው ልጅ የተለየ አፈጣጠር፣ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል (ዘፍ. 1፡26-27) እናም በግል "የተበጀ/የተሠራ" በእግዚአብሔር (ዘፍ. 2፡7)፣ እሱን አድርጎታል
1. ሥጋዊ ፍጥረት፣ በምድር ላይ እንዳሉ እንደ ሌሎች እንስሳት (ኔፊሽ)
2. መንፈሳዊ ፍጥረት፣ በተለየ መልኩ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት እንዲኖረው የተደረገ፤ ይህ መንፈሳዊ ገጽታ በበርካታ ዘይቤዎች/ምሳሌዎች/ቃላት ይገለጻል
   ሀ. ልብ፣ ማለትም፣ መዝ. 36:1፤ 39:3፤ 55:4፤ 109:22
   ለ. ኩላሊት/አንጀት፣ ማለትም፣ መዝ. 22:14፤ ኤር. 4:19፤ 31:20፤ ሰቆ. 1:20፤ 2:11

ሐ. መንፈስ፣ ማለትም፣ ኢሳ. 57:16፤ ዘካ. 12:1
መ. ሐሳብ፣ መዝ. 94:19

▣ **"መንፈስ"** ቃሉ (ቢዲቢ 924) በዚህ መዝሙር ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል።
1. "የቀና መንፈስ፣" 51:10
2. "ቅዱሱን መንፈስህን፣" 51:11
3. "በእሽታ መንፈስ፣" 51:12
4. "የተሰበረ መንፈስ፣" 51:17

## ልዩ ርዕስ፡ መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ

I. የግሪክ ቃላት
  ሀ. *pneō* ፣ መተንፈስ
  ለ. *pnoē*፣ ነፋስ፣ እስትንፋስ
  ሐ. *pneuma*፣ መንፈስ፣ ነፋስ
  መ. *pneumatik*os፣ ከመንፈስ የሆነ
  ሠ. *pneumatikōs*፣ በመንፈሳዊነት
II. የግሪክ ፍልስፍናዊ ዳራ (*pneuma*)
  ሀ. አርስቶትል ቃሉን የሚጠቀምበት እንደ ሕይወት ኃይል ነው፣ ከልደት እስከ ራስን እስከ መግዛት (መቆጣጠር) ድረስ የሚያድግ
  ለ. ስቶይክስ (ምሑራን) ቃሉን የሚጠቀሙበት እንደ *uchē*፣ (ነፍስ) ተመሳሳይ ነው፣ ብሎም *nous* (አእምሮ) ከአምስቱ የስሜት አካላት አኳያ እና ከሰው እውቀት ጋር
  ሐ. የግሪክ አስተሳሰብ — ቃሉ ለመለኮታዊ ድርጊት አቻ ነው (ማለትም፣ መናፍስት ጠሪነት፣ አስማት፣ ምሥጢራዊ፣ ትንቢት፣ ወዘተ)
III. ብሉይ ኪዳን (*ruah*)
  ሀ. የአሀዳዊው አምላክ ድርጊቶች (ማለትም፣ መንፈስ፣ 90 ጊዜ ያህል በብኪ ጥቅም ላይ የዋለ)
    1. በአዎንታ፣ ዘፍጥረት 1፡2
    2. በአሉታ፣ 1 ሳሙ.16:14-16፣23፤ 1 ነገ. 22:21-22፤ ኢሳ. 29:10
  ለ. አምላክ-ሰጥ የሕይወት ኃይል በሰው (ማለትም፣ የእግዚአብሔር እስትንፋስ፣ ዘፍ. 2:7)
  ሐ. ሴፕቱዋጂንት *ruahን እንደ pneuma* ይተረጉመዋል (100 ጊዜ ያህል በLXX ጥቅም ላይ የዋለ)
  መ. በኋለኞቹ ራቢያዊ ጽሑፎች፣ የአፖካሊፕቲክ ጽሑፍ እና የሙት ባሕር ጥቅሎች፣ የዞሮአስትሪአኒዝም ተጽዕኖ አለባቸው፣ (*pneuma*) ለመላእክትና ለአጋንንት ጥቅም ላይ ውሏል
IV. አዲስ ኪዳን (*pneuma*)
  ሀ. የእግዚአብሔር የተለየ መገኘት፣ ኃይል፣ እና ማብቃት
  ለ. መንፈስ ቅዱስ ከእግዚአብሔር የቤተ ክርስቲያን ሥራ ጋር ይያያዛል
    1. ትንቢት
    2. ተአምር
    3. ወንጌልን ለማወጅ ግልጽነት
    4. ጥበብ (ማለትም፣ ወንጌል)
    5. ደስታ
    6. በአዲሱ ዘመን የመጣ
    7. መለወጥ (ማለትም፣ መቃተት እና ማደር)
    8. ክርስቶስን መምሰል
    9. የአገልግሎት ልዩ ተሰጥዖ
    10. ለአማኞች ይጸልያል

  መንፈስ የሰው ልጅን ፍላጎት ያነቃል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚኖረው ኅብረት፣ ይኸውም ለተፈጠሩበት። ይኸም ኅብረት ይቻላል፣ በኢየሱስ፣ በእግዚአብሔር መሢሕ ማንነትና ሥራ። አዲሱ መንፈሳዊ ንቃት ክርስቶስን ወደ መምሰል፣ አገልግሎት፣ እና እምነት ሕይወት ያመራል።

  ሐ. ጊዜ ለማይወስነው መንፈሳዊ የተሻለ መረዳት፣ ከመንፈስ ቅዱስ ጋር በአንደኛው ዳር፣ እና የሰው ልጅ በዚህ ዓለም እንዳለ ሥጋዊ ፍጥረት፣ ግን ደግሞ መንፈሳዊ ፍጥረት፣ በእግዚአብሔር አምሳል፣ በሌለኛው ዳር።
  መ. ጳውሎስ የአኪ ደራሲ ነው፣ እሱም የመንፈስ ቅዱስ/መንፈስ ሥነ-መለኮትን ያዳበረ።
    1. ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስን ተጠቅሟል ሥጋን ለመቃረን (ማለትም፣ የኃጢአት ተፈጥሮ)
    2. ጳውሎስ መንፈስን ተጠቅሟል ሥጋዊነትን ለመቃረን
    3. ጳውሎስ መንፈስ ቅዱስ/መንፈስን ተጠቅሟል፣ የሰውን አስተሳሰብ፣ እውቀት፣ እና ሕላዊ ለመቃረን
  ሠ. አንዳንድ ምሳሌዎች ከ 1 ቆሮንቶስ
    1. መንፈስ ቅዱስ፣ 12፡3
    2. የእግዚአብሔር ኃይልና ጥበብ በመንፈስ ቅዱስ ይገለጣል፣ 2፡4-5
    3. የእግዚአብሔር ድርጊቶች በአማኙ ውስጥ
      ሀ. አዲስ ሐሳብ ያበጃል፣ 2:12፤ 14:14፣32
      ለ. አዲስ መቅደስ፣ 3:16፤ 6:19-20
      ሐ. አዲስ ሕይወት (ማለትም፣ ሞራላዊ)፣ 6:9-11

መ. አዲስ ሕይወት በጥምቀት ተምሳሌት፣ 12:13
ሠ. ከእግዚአብሔር ጋር አንድ መሆን (ማለትም፣ መለወጥ)፣ 6:17
ረ. የእግዚአብሔር ጥበብ፣ የዓለም ጥበብ ሳይሆን፣ 2:12-15፤ 14:14፣32፣37
ሰ. መንፈሳዊ ተውህቦ (ስጦታ) ለእያንዳንዱ አማኝ፣ ለአገልግሎት፣ ምዕራፍ 12 እና 14
4. መንፈሳዊው ከሥጋዊው ጋር ተቃርኗል፣ 9:11፤ 10:3፤ 15:44
5. መንፈሳዊው ዓለም፣ ከሥጋዊው ዓለም ጋር ተቃርኗል፣ 2:11፤ 5:5፤ 7:34፤ 15:45፤ 16:18
6. የሰዎችን መንፈሳዊ/ውስጣዊ ሕይወት የመጥቀሻ መንገድ፣ ከሥጋዊ አካል የተለየ መሆኑን፣ 7:34

ረ. ሰዎች በፍጥረታቸው በሁለት ዓለማት ይኖራሉ (ማለትም፣ መንፈሳዊ እና ሥጋዊ)። የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ጋር ካለው ቅርብ ወዳጅነት ወድቋል (ዘፍጥረት 3)። በክርስቶስ ሕይወት፣ ትምህርት፣ ሞት፣ ትንሣኤ፣ እና የመመለሱ ተስፋ፣ መንፈስ ቅዱስ ለወደቁ ሰዎች ይቃትታል፣ እምነትን በወንጌል ይለማመዱ ዘንድ፣ በየትኛው ነጥብ እነርሱ እንደሚመለሱ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ወዳለው ኅብረት። መንፈስ ቅዱስ የሥላሴ አካል ነው፣ እርሱም አዲሱን የጽድቅ ዘመን ያበጀ። መንፈስ ቅዱስ የእግዚአብሔር አብ ወኪል እና የወልድ ወጋኝ ነው በዚህ "ዘመን።" ችግሩ ይኖራል፣ አዲሱ ዘመን በጊዜው በመሆኑ ምክንያት፣ አሮጌው ዘመን እሱም የኃጢአት ዓመጻ አሁንም ገና በመኖሩ። መንፈስ ቅዱስ አሮጌውን ወደ አዲስ ይቀይረዋል፣ ምንም እንኳ ሁለቱም ቢኖሩም።

**51፡11ለ** ብዙዎቹ አታቾች ያምናሉ፣ ይህ የቅኔ ስንኝ 1 ሳሙ.11:6፤ 16:14፤ 18:12ን እንደሚያመለክት፣ እዚያም ሳኦል በመነሻው መንፈስ ቅዱስ እንዳለበት፣ ነገር ግን ከተደጋጋሚ ኃጢአቱ በኋላ መንፈስ ቅዱስ ተወው እና ወደ ዳዊት ሄደ።

የእኔ የራሴ ማኅበረ ምዕመናን ይሄንን መዝሙር፣ በተለይም ቁጥር 12ን የሚጠቀምበት፣ ማንም ደኅንነቱን እንደማያጣ ለማስረገጥ ነው፣ ምክንያቱም እሱ "የማዳንህን ደስታ ስጠኝ" ስለሚል። ሆኖም፣ የሳኦል መንፈሳዊ ይዞታ ርግጠኛ አይደለም። እኔ እነዚህን ጉዳዮች በተመለከተ ቢያንስ የራሴ መረዳት እንዲሆን የመረጥኩት

1. እናንተን አመለከታችኋለሁ፣ ልዩ ርዕስ፡ ክህደት መዝ. 26፡8-12
2. እናንተን አመለከታችኋለሁ፣ ልዩ ርዕስ፡ ጽናት መዝ. 7:12 ላይ
3. ቀጣዩን ልዩ ርዕስ አስገባለሁ፡ ዋስትና (ከታች ተመልከት)

## ልዩ ርዕስ፡ ማረጋገጫ

ሀ. ክርስቲያኖች እንደዳኑ ያውቃሉን (1 ዮሐንስ 5፡13)? ዮሐንስ ሦስት መፈተሻዎች ወይም ማስረጃዎች አሉት።
1. ዶክትሪናዊ (እምነት) (ቁ. 1፣5፣10፤ 2:18-25፤ 4:1-6፣14-16፤ 5:11-12)
2. የሕይወት ስልት (ታዛዥነት) (ቁ. 2-3፤ 2:3-6፤ 3:1-10፤ 5:18)
3. ማኅበራዊ (ፍቅር) (ቁ፣ 2-3፤ 2:7-11፤ 3:11-18፤ 4:7-12፣ 16-21)

ለ. ዋስትና ክፍለ-ሃይማኖታዊ ጉዳይ ሆኗል
1. ጆን ካልቪን ዋስትናን የሚመሠርተው በእግዚአብሔር ምርጫ ላይ ነው። እሱ የሚለው በዚህ ሕይወት ፈጽሞ ርግጠኞች መሆን አንችልም።
2. ጆን ዌስሊ ዋስትናን የሚመሠርተው በሃይማኖታዊ ልምምዶች ላይ ነው። እሱ የሚያምነው፣ እኛ ከሚታወቀው ኃጢአት በላይ ልንኖር እንደምንችል ነው።
3. ሮሜ ካቶሊክ እና የክርስቶስ ቤተ-ክርስቲያን ዋስትናን የሚመሠርቱት ሥልጣን ባላት ቤተ-ክርስቲያን ነው። አንዱ የሚሆንበት ቡድን ለዋስትና ቁልፍ ጉዳይ ነው።
4. አብዛኞቹ ወንጌላውያን ዋስትናን የሚመሠርቱት በመጽሐፍ ቅዱስ ተስፋዎች ላይ ነው፣ በአማኙ ሕይወት ከሚታዩ የመንፈስ ፍሬዎች ጋር በተያያዘ (ገላ. 5:22-23)።

ሐ. እኔ የማስበው ለወደቀው የሰው ልጅ ቀዳሚ ዋስትናው የተያያዘው በሦስትነቱ አንድ ከሆነው አምላክ ጋር ነው።
1. የእግዚአብሔር አብ ፍቅር
   ሀ. ዮሐንስ 3:16፤ 10:28-29
   ለ. ሮሜ 8:31-39
   ሐ. ኤፌሶን 2:5፣8-9
   መ. ፊሊጵስዩስ 1:6
   ሠ. 1 ጴጥሮስ 1:3-5
   ረ. 1 ዮሐንስ 4:7-21
2. የእግዚአብሔር ወልድ ድርጊቶች
   ሀ. በእኛ ምትክ መሞት
      1) ሐዋ. 2:23
      2) ሮሜ 5:6-11
      3) 2 ቆሮንቶስ 5:21
      4) 1 ዮሐንስ 2:2፤ 4:9-10
   ለ. የሊቃነ ክህነት ጸሎት (ዮሐንስ 17:12)
   ሐ. ቀጣይነት ያለው ምልጃ
      1) ሮሜ 8:34
      2) ዕብራውያን 7:25
      3) 1 ዮሐንስ 2:1
3. የእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ አገልግሎት

ሀ. መጥራት (ዮሐንስ 6:44፣65)
ለ. ማተም
1) 2 ቆሮንቶስ 1:22፤ 5:5
2) ኤፌሶን 1:13-14፤ 4:3
ሐ. ማረጋገጥ
1) ሮሜ 8:16-17
2) 1 ዮሐንስ 5:7-13

መ. ነገር ግን ሰዎች የግድ ምላሽ መስጠት ይኖርባቸዋል፣ ለእግዚአብሔር ኪዳናዊ ስጦታ (በሁለቱም፣ በመነሻም ሆነ በቀጣይነት)
1. አማኞች የግድ ከኃጢአት መመለስ ይኖርባቸዋል (ንስሐ) እና ወደ እግዚአብሔር በኢየሱስ በኩል (እምነት)
ሀ. ማርቆስ 1:15
ለ. ሐዋ 3:16፣19፤ 20:21
2. አማኞች የግድ እግዚአብሔር በክርስቶስ ያደረገውን ስጦታ መቀበል ይኖርባቸዋል
ሀ. ዮሐንስ 1:12፤ 3:16
ለ. ሮሜ 5:1 (እና በተምሳሌት 10:9-13)
ሐ. ኤፌሶን 2:5፣8-9
3. አማኞች በእምነት የግድ መቀጠል ይኖርባቸዋል
ሀ. ማርቆስ 13:13
ለ. 1 ቆሮንቶስ 15:2
ሐ. ገላትያ 6:9
መ. ዕብራውያን 3:14
ሠ. 2 ጴጥሮስ 1:10
ረ. ይሁዳ 20-21
ሰ. ራዕይ 2:2-3፣7፣10፣17፣19፣25-26፤ 3:5፣10፣11፣21
4. አማኞች ሦስት ፈተናዎች ይገጥማቸዋል
ሀ. ዶክትሪናዊ (ቁ. 1፣5፣10፤ 2:18-25፤ 4:1-6፣14-16)
ለ. የሕይወት ስልት(ቁ. 2-3፤ 2:3-6፤ 3:1-10)
ሐ. ማኅበራዊ (ቁ፣ 2-3፤ 2:7-11፤ 3:11-18፤ 4:7-12፣ 16-21)

ሠ. ዋስትና አስቸጋሪ ነው፣ ምክንያቱም
1. አማኞች ዘወትር ሌሎች ልምምዶችን ይሻሉ፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ቃል ያልተገቡ
2. አማኞች ዘወትር ወንጌልን በሙላት አይረዱትም
3. አማኞች ዘወትር በፍቃዳቸው ኃጢአት መሥራታቸውን ይቀጥላሉ (1 ቆሮ. 3:10-15፤ 9:27፤ 1 ጢሞ. 1:19-20፤ 2 ጢሞ. 4:10፤ 2ጴጥ. 1:8-11)
4. አንዳንድ ግላዊ ዓይነቶች (ማለትም፣ ፍጹማውያን) የእግዚአብሔርን ከሁኔታ ውጭ የሆነ ተቀባይነት እና ፍቅር ፈጽሞ ሊቀበሉ አይችሉም
5. በመጽሐፍ ቅዱስ የተሳሳቱ እምነቶች ምሳሌዎች አሉ (ማቴ. 13:3-23፤ 7:21-23፤ ማርቆስ 4:14-20፤ 2 ጴጥ. 2:19-20፤ 1ዮሐንስ 2:18-19)

▣ ***"ቅዱሱ መንፈስህ"*** በብኪ ባብዛኛው፣ *"መንፈስ"* የእግዚአብሔር ኃይል ነው (ማለትም፣ ዘፍ. 1:2)፣ የተለየ አካል ሳይሆን (ግን ኢሳ. 63፡10-11 እይ)። ሆኖም፣ ይህ የመንፈስ አካልነት ጽንሰ-ሐሳብ በአኪ ዳብሯል። ሁለት ልዩ ርዕሶች ነጥቡን ለማብራራት ይረዳሉ።

## ልዩ ርዕስ፡ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት

በብኪ "የእግዚአብሔር መንፈስ" (ማለትም፣ *ruach*) የያህዌህን ዓላማ የሚፈጽም ኃይል ነበር፣ አካል ለመሆኑ ግን ምንም ፍንጭ አልነበረም (ማለትም፣ የብኪ አሀዳዊነት monotheism)። ሆኖም፣ በአዲስ ኪዳን የመንፈስ ቅዱስ ሙሉ አካልና አካላዊነት ተመዝግቧል።

1. የማይገባ ነገር ሊባል ይችላል (ስድብ) (ማቴ. 12:31፤ ማርቆስ 3:29)
2. ያስተምራል (ሉቃስ 12:12፤ ዮሐንስ 14:26)
3. ይመሰክራል (ዮሐንስ 15:26)
4. ይወቅሳል፣ ይመራል (ዮሐንስ 16:7-15)
5. "ማን" ተብሎ ይጠራል (ማለትም፣ *hos*) (ኤፌ. 1:14)
6. ሊያዝን ይችላል (ኤፌ. 4:30)
7. ሊጠፋ ይችላል (1ተሰ. 5:19)

ሥላሴአዊ ጽሑፎች ደግሞ ስለ ሦስቱ አካላት ይናገራሉ።

1. ማቴ. 28:19
2. 2ቆሮ. 13:14
3. 1ጴጥ. 1:2

መንፈስ ከሰው ተግባር ጋር ተያያዥነት አለው።

1. ሐዋ. 15:28
2. ሮሜ. 8:26

3. 1ቆሮ. 12:11
4. ኤፌ. 4:30

ገና በሐዋርያት ሥራ መጀመሪያ ላይ የመንፈስ ቅዱስ ሚና አጽንዖት ተሰጥቶታል። ጰንጠቆስጤ የመንፈስ ቅዱስ ሥራ መጀመሪያ አልነበረም፣ ግን የአዲስ ምዕራፍ እንጂ። ኢየሱስ ሁሌም መንፈስ ነበረበት። የእሱ ጥምቀት የመንፈስ ሥራ መጀመሪያ አልነበረም፣ ግን የአዲስ ምዕራፍ አንጂ። ሉቃስ ቤተ-ክርስቲያንን የተሳካ አገልግሎት ላለው አዲስ ምዕራፍ ያዘጋጅ ነበር። ኢየሱስ አሁንም አትኩሮት ነው፣ መንፈስ አሁንም ውጤታማ አግባብ ነው፣ እንዲሁም የአብ ፍቅር፣ ይቅር ባይነት፣ እና በአምሳሉ የተፈጠሩት ሰዎች መመለስ ግብ ነው!

## ልዩ ርዕስ፡ ሥላሴ

የሥላሴን ሦስት አካላት እንቅስቃሴ በአንድ ወጥ በሆነ አውደ ተመልከታቸው፡፡ «ስላሴ» የሚለው መጠሪያ ለመጀመሪያ ጊዜ የተፈጠረው በቱርቱስያን እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ቃል አይደለም፡፡ ነገር ግን ሐሳቡ በጣም የተስፋፋ ነው፡፡

ሀ. ወንጌላት

1. ማቴ 3:16-17፤ 28:29 (እና ሌሎች ተመሳሳዮች)
2. ዮሐ 14:26

ለ. ሐዋርያት ሥራ - ሐዋ 2:32-33፤ 38-39

ሐ. ጳውሎስ

1. ሮሜ 1:4-5፤ 5:1፡5፤ 8:1-4፡8-10
2. 1ቆሮ 2:8-10፤ 12:4-6
3. 2ቆሮ 1:21: 13:14
4. ገላ 4:4-6
5. ኤፌ 1:3-14፣ 17፤ 2:18፤3:14-17፤ 4:4-6
6. 1ተሰ 1:2-5
7. 2ተሰ 2:13
8. ቲቶ 3:4-6

መ. ጴጥሮስ 1ጴጥ 1:2

ሠ. ይሁዳ ቁ. 20-21

በእግዚብሔር ውስጥ የብዙ ቁጥር መኖሩ በብሉይ ኪዳን ውስጥ ፍንጭ አለ፡፡

ሀ.የብዙ ቁጥር ለእግዚአብሔር መጠቀሱ

1. “ኤሎሂም” የሚለው ስም ብዙ ቁጥሮችን አመልካች ነው፡፡ ግን ምን ጊዜም በእግዚአብሔር ሲጠቀም ነጠላ ግስን አመልካች ነው፡፡
2. “እኛ” በዘፍጥረት 1፡26-27፣ 3፡22፣ 11፡7

ለ. የእግዚአብሔር መልአክ መለኮትን በሚታይ መልኩ የወከለ ነበር

1. ዘፍ. 16፡7-13፣ 22፡11-15፣ 31፡11፣13፣ 48፤15-16
2. ዘፀ. 3፡2፣4፤ 13፡21፤ 14፡19
3. መሳፍንት 2፡1፣ 6፡2-23፤ 13፡3-22
4. ዘካሪያስ 3፡1-2

ሐ. እግዚአብሔር እና መንፈሱ የተለያዩ (ዘፍ1:1-2 መዝ 104:30፤ ኢሳ 63: 9-11፤ ሕዝ 37:13-14)

መ. እግዚአብሔር (ያህዌህ) እና መሲል (አዶናይ) የተለያዩ ናቸው መዝ 45:6-7፤ 110:1፤ ዘካ 2:8-11፤ 10:9-12

ሠ. መሲሑ እና መንፈስ የተያዩ ናቸው፤ ዘካ 12:10

ረ. ሦስቱም በኢሳ 48:16፤ 61:1 ላይ ተጠቅሰዋል፡፡

የኢየሱስ መለኮትነት እና የመንፈስ ስብእና አጥባቂ እና የአንድ አምላክ አምልኰ ተከታዮች ለነበሩት ለቀደሙት አማኞች ችግር የፈጠረባቸው ጉዳይ ነበር፡፡

1. ቱርቱሊያን - ወልድ ከአብ እንደሚያንስ አስረዳ
2. ኦሪገን - የወልድን እና የመንፈስ መለኰታዊ ማንነት ዝቅ አደረገ
3. አርዮስ - የወልድን እና የመንፈስ መለኰትነት ካደ
4. ምናርኪያኒዝም - አንድ አምላክ ተከታታይነት ባው ሁኔታ እንደ አባት፣ ልጅ፣ አና መንፈስ እንደ ተገለጠ የሚያምን

ስላሴ በታሪክ ሁሉ በቅዱሳት መፃህፍት አማካኝነት ሃሳቡ ሲገለፅ የኖረ ጉዳይ ነው፡፡

1. የኢየሱስ መለኰትነት፣ ከአብ ጋር እኩል መሆኑ በ325 ዓ.ም በኒቅያ ጉባኤ ፀደቀ
2. የመንፈስ ሙሉ ስብእና እና መለኰትነት ከአብ እና ከወልድ ጋር አኩል መሆኑ በኮንስታንቲኖፕል ጉባኤ (381 ዓ.ም) ፀድቋል፡፡
3. የስላሴ አስተምህሮ የአውግስቲን ሥራ በሆነው ውስጥ *Deirጰitae* በሙላት ተገልጿል፡፡

እዚህ ላይ ግን እንቆቅልሽ የሆነ ጉዳይ አለ፡፡ አዲስ ኪዳን ግን አንድ መለኰታዊ መንነት ያለው እና ሦስት ዘላለማዊ የስብእና መገለጦች እንዳሉት የሚያረጋግጥ ይመስላል፡፡

## መዝሙር ፡ 51፡14-17

**[14]የመድኃኒቴ አምላክ እግዚአብሔር ሆይ፥ ከደም አድነኝ፥**

**አንደበቴም በአንተ ጽድቅ ትደሰታለች።**
**[15]አቤቱ፥ ከንፈሮቼን ክፈት፥**
**አፌም ምስጋናህን ያወራል።**
**[16]መሥዋዕትን ብትወድድስ በሰጠሁህ ነበር**
**የሚቃጠለውም መሥዋዕት ደስ አያሰኝህም።**
**[17]የእግዚአብሔር መሥዋዕት የተሰበረ መንፈስ ነው፥**
**የተሰበረውንና የተዋረደውን ልብ እግዚአብሔር አይንቅም።**

**51፡14-17** ይህ አንጓ አስተሳሰቡን ይቀጥላል

1. ማዳን — ቢ.ዲ.ቢ. 664፣ ኬቢ. 717፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ መዝሙረኛው ኃጢአተኛ ነበር፣ ይቅርታ እንዲደረግለት ያስፈልገዋል። ቁጥር 14 ዳዊት ኦርዮን ከመግደሉ ጋር ይያያዛል ("ደም፣" ቢ.ዲ.ቢ. 196፣ የሚያመለክተውም "የደም ማፍሰስ ኃጢአት"ን ይመስላል፣ ማለትም "ንጹሕ ሰውን መግደል")።
2. "ሕግ ተላላፎችን ማስተማር" (ቢ.ዲ.ቢ. 540፣ ኬቢ. 531፣ ፔል ተኳዳኝ) የቁ. 13ሀ ተብራርቷል/ ተገልጿል
   ሀ. አንደበቴ በደስታ ይዘምራል (ዳዊት ዘማሪ ነበር) የአንተን ጽድቅ (ይህ ቁልፍ ቃል [ቢ.ዲ.ቢ. 842] መሠረታዊ ፍችው መደበኛ፣ ማስመሪያ፣ ቀጥተኛ ጠርዝ ማለት ነው። ሁሉም ለ"ኃጢአት" የሆኑት ቃላት ከመደበኛው ማፈንገጥ ናቸው፤ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ያለው ፍቺ "መከላከያ" ወይም "ተገቢ ድርጊቶች" ነው፣ መዝ. 71፡2፣15፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡5 ላይ)።
      (1) አንደበቴን እከፍታለሁ
      (2) አፌም ምስጋናህን ያወራል

አዲሱ አስተሳሰብ 51፡16-17 ላይ ይጀምራል። ምንም ዓይነት የተዘረዘረ መሥዋዕት የለም ሌዋውያን 1-7 ላይ፣ ሆን ተብሎ፣ ቀድሞ ለታሰበበት ኃጢአት (ሌዋ. 4:2፣22፣27፤ 5:15-18፤ 22:14፤ ዘኍ. 15:27-28)። ቢኖር ኖሮ ይሰጥ (ያቀርብ) ነበር (ቢ.ዲ.ቢ. 678፣ ኬቢ. 733፣ ቃል ተኳዳኝ)፣ ነገር ግን አልነበረም፣ ስለዚህ ራሱን በእግዚአብሔር ምሕረት ላይ ጣለ። እሱ ታመነ/አመነ እግዚአብሔር እንደማይተወው (ሁለቱም ኒፋል አንቀጾች)

1. የተሰበረ ልብ በኃጢአት ላይ (ቢ.ዲ.ቢ. 990፣ መዝ. 34:19፤ ኢሳ. 61:1፤ ኤር. 23:9)
2. የተጸጸተ ልብ ("የተሰበረ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 194፣ ኢሳ. 57:15)

ይህም የሮሜ 12:1-2 ዓይነቱን አምላኪ ይጠቅሳል። ንስሐ በእግዚአብሔር ላይ ተጽዕኖ አለው (መዝ. 34:18)!

**51:15**
**አአመመቅ (1970)** **"ጌታ"**
**አአመመቅ (1995)** **"ጌታ"**

ኤምቲ አዶን የሚል አለው፣ ያህዌ ሳይሆን። የእስራኤል አምላክ የኪዳን ስም መዝሙር ላይ በመጽሐፍ II እንደ መጽሐፍ I በተደጋጋሚ አይገኝም። አንዳንድ ሊቃውንት የሚገምቱት የመጽሐፍ II አጠናቃሪ አብዛኞቹን የያህዌ ጠቃሾች ወደ ኤሎሂም እንደ ቀየረ ነው።

**መዝሙር ፡ 51፡18-19**

**18አቤቱ፥ በውዴታህ ጽዮንን አሰማምራት**
**የኢየሩሳሌምንም ቅጽሮች ሥራ።**
**19የጽድቁን መሥዋዕት መባውንም**
**የሚቃጠለውንም መሥዋዕት በወደድህ ጊዜ፥**
**ያን ጊዜ በመሠዊያህ ላይ ፍሪዳዎችን ይሠዋሉ።**

**51፡18-19** መዝሙሩ በተለየ አስተሳሰብ የሚዘጋ ይመስላል። ያልተጠበቀ ለውጥ ይታያል፣ ከአንድ ግለሰብ ወደ ብሔራዊ ጸሎት፣ ለእግዚአብሔር በረከት ("መልካም አድርግ፣" ቢ.ዲ.ቢ. 405፣ ኬቢ. 408፣ ሂፊል ተተኳሪ) በኢየሩሳሌም። ጸሎቱ የሚያመለክተው ኢየሩሳሌም ችግሮች እንዳለባት ነው።

1. ቅጽሮች ሥራ
2. መሥዋዕታዊ ሥርዓቷን መልስ

ብዙዎቹ ሊታኞች ቁጥር 16ን የሚጠቀሙት መሥዋዕትን ለማንኳሰስ ነው፣ ነገር ግን ከ51፡23 የተነሣ ማየቱ የተሻለ የሚሆነው በ"ሆን ተብሎ" እና "ያለ ማወቅ" ኃጢአት መካከል ያለውን ልዩነት አጽንዖት ለመስጠት ነው።

ደግሞም እነዚህ ሁለት ቁጥሮች ከዳዊት ሕይወት ጋር መቼም ጊዜ ቢሆን አለመግጠማቸውን ተገንዘብ። ምንም ዓይነት የኤምኤስኤስ ማስረጃ የለም፣ እነርሱ መዝሙርን ከመጻፍ ወይም ማጠናቀር በኋላ የተጨመሩ ለመሆናቸው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙረኛው እግዚአብሔር እንዲራራለት ሁለት ምክንያቶችን ይሰጣል። እነርሱ እነማን ናቸው፣ ጠቃሚ የሆኑትስ ለምንድነው?
2. በዚህ መዝሙር ላይ ይቅርታን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን የተለያዩ ቃላት ዘርዝር።
3. ቁጥር 4ን በራስህ ቋንቋ አብራራ።
4. ቁጥር 5 ምን ማለት ነው፣ በብኪ መቼት?
5. እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስን ከኃጢአተኞች ላይ ይወስዳልን?
6. ቁጥር 16-17 ከቁጥር 19 ጋር ያላቸውን ግንኙነት አብራራ። በ“ሆን ተብሎ የተደረገ ኃጢአት” እና “ሆን ተብሎ ባልተደረገ ኃጢአት” መካከል ያለውን ልዩነት አብራራ፣ ከመሥዋዕታዊው ሥርዓት ጋር በተያያዘ።
7. ቁጥር 18-19 ከቀሪው መዝሙር ጋር እንዴት ይዛመዳል?

# መዝሙር 52
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የትምክህት ኃጢአት ከንቱነት<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት ትምህርት፤ ኤዶማዊው ዶይቅ ለሳኦል መጥቶ በነገረው ጊዜ፤ “ዳዊት ወደ አቤሜሌክ ቤት መጥቷል” ብሎ። | የኃጢአተኛ ፍጻሜና የጻድቅ ሰላም | የእግዚአብሔር ፍርድ በጨካኝ ላይ ስለመቃረቡ | የእግዚአብሔር ፍርድና ጸጋ | የክፉ ዕጣ ፈንታ |
| 52:1-4 | | | | |
| | 52:1-4 | 52:1-4 | 52:1-4 | 52:1-2 |
| 52:5-7 | | | | 52:3-4 |
| | 52:5-7 | 52:5-7 | 52:5-7 | 52:5 |
| 52:8-9 | | | | 52:6-7 |
| | 52:8-9 | 52:8-9 | 52:8-9 | 52:8 |
| | | | | 52:9 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የሚመለከተው ክፉ ሰዎችን እንደሆነ ተገንዘብ (የወል ነጠላ ቁጥር አጠቃቀም)። አብዛኞቹ መዝሙሮች የተመለከቱት ለእግዚአብሔር ነው።

ለ. ይህ መዝሙር ተለጣጣቂ አንጓዎች ነው፣ እሱም የኃጢአተኞችን የማይመች ሁኔታ ከጻድቅ ደኅንነት ጋር የሚያነጻጽር (የሚያቃርን)።

ሐ. የሁለት ወገኖች ንግግር መሆኑን እነርሱም ልባቸውን የሚገልጡ መሆኑን ተገንዘብ (የውስጥ ሐሳብ፣ ማቴ. 12፡34-37)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 52፡1-4**
**[1]ኃያል ሆይ፥ በክፋት ለምን ትኳደዳለህ?**
**ሁልጊዜስ በመተላለፍ?**
**[2]እንደበትህ ኃጢአትን ያስባል**
**እንደ ተሳለ ምላጭ ሸንገላን አደረግህ።**
**[3]ከመልካም ይልቅ ክፋትን፥**
**ጽድቅንም ከመናገር ይልቅ ዓመፃን ወደድህ። ሴላህ**

[4]**የሚያጠፉ ቃልን ሁሉ፥**
**የሽንገላ ምላስን ወደድህ።**

**52፡1** ይህ ተቃርኗዊ ትይዩ ነው። በመዝሙር ሙሉ ኃጢአተኛና ጻድቅ ተቃርነዋል (ጄፒኤስኦኤ)። ፔሺታ፣ ኤምቲን አዙሮ "ቀኑን ሙሉ በጻድቅ ላይ" በሚል አስፍሯል።

LXX ሙሉው ቁጥር "ኃጢአተኛ"ን እንዲያመለክት አድርጓል። ሁለተኛው ስንኝ "ቀኑን ሁሉ በዓመጻኝነት" የሚል አለው። ኤቢ (ገጽ 11) ሁለተኛውን ስንኝ ውስጠ-ወይራ ያደርገዋል፣ "ኦ ለኤል የተሰጠህ።"

◘ **"መኳደድ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፤ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*) በ*ሂፊል* ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ራስን ለመወደስ ነው (1 ነገ. 20፡11፤ መዝ. 49፡6፤ ምሳ. 20፡14፤ 27፡1፤ ኤር. 49፡4)። ኤር. 9፡23-24 ላይ ቃሉ ሁለቱንም ነው ያለው፣ አሉታዊ (የውሸት መኳደድ) እና አዎንታዊ (ለመኳደድ እውነተኛ መሠረት) ገጽታዎች።

◘ **"ኃያል ሆይ"** ይህ ከሦስቱ አንደኛው አመላካች ስም ነው፣ ኃጢአተኛ ሰዎችን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ።

1. ኃያል ሆይ – ቢዲቢ 150፣ እነርሱ ኃያል ናቸው፣ ስለ ኃጢአታቸው በመመካት፤ ይህ ቆጥቋጭ ስላቅ ነው
2. ማሳትን የምትሠራ ሆይ – ቢዲቢ 793 I አወቃቀር ቢዲቢ 941 I
3. ሐሰተኛ አንደበት ሆይ – ቢዲቢ 546 አወቃቀር 941፤ እንደ ቁ. 2 ተመሳሳይ ሥር ያይደለ፣ ነገር ግን እጅግ የሚቀርብ (ማለትም፣ ሰውኛ ክፉ ንግግር)

◘ **"መልካም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 5፡7 ላይ።

◘ **"ሁልጊዜ"** ይህ የሚያመለክተው የተራዘመ ጊዜን ነው (ማለትም፣ ዘላለም)። "የዘላለም" ጽንሰ-ሐሳብ በርካታ ጊዜ ተደጋግሟል፣ በዚህ መዝሙር ላይ።

1. የእግዚአብሔር ፍርድ — ቁ. 5ሀ
2. ጻድቅ በእግዚአብሔር ቸርነት ይታመናል — 52፡8ለ
3. ጻድቅ ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረቡ — 52፡9ሀ

**52፡2** ቃላት ዋነኛ ነገር እንደሆኑ ማስታወስ ይገባናል። እነርሱ ሊባርኩ ወይም ሊረግሙ ይችላሉ (ያዕቆብ 3፡1-12)። በቃላት ላይ ኃይል አለ (ዝኪ. ቁ. 4)። በእግዚአብሔር ፊት ምላሽ እንሰጣለን፣ ስለ ቃላችን (ማቴ. 12፡34-37)። ንግግር ልብን ይገልጣል።

## ልዩ ርዕስ፡ የሰው ንግግር

I. የመክፈቻ አስተሳሰቦች ከምሳሌ
- ሀ. ቋንቋ በሰው ልጅ የእግዚአብሔር አምሳል ክፍል ነው (ማለትም፣ ፍጥረት ወደ ሕላዌ የመጣው በንግግር ነው እግዚአብሔርም ለፍጥረቱ ሰው ተናግሯል)። እሱም የእኛ ሰውነት ዓይነተኛ ክፍል ነው።
- ለ. የሰው ንግግር ከሌሎች ሰዎች ጋር እንድንግባባ ያደርገናል፣ ስለ ሕይወት ምን እንደሚሰማን በመግለጽ። ስለዚህ፣ እሱ በርግጥ ማን እንደሆንን ይገልጣል (ምሳ. 18፡2፤ 4፡23 [20-27])። ንግግር የግለሰብ መመርመሪያ ብልሃት ነው (ምሳ. 23፡7)።
- ሐ. እኛ ማኅበራዊ ፍጥረቶች ነን። እኛ ለመቀበልና ለማጽናት የሚገደን ነን። እሱንም ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ባልንጀሮቻችን እንሻዋለን። ቃላት እነዚህን መሻቶች ለማሳካት ኃይል አላቸው፣ በሁለቱም በአዎንታዊ (ምሳ. 17፡10) እና በአሉታዊ (ምሳ. 12፡18) መንገዶች።
- መ. በሰዎች ንግግር ብርቱ ኃይል አለ (ምሳ. 18፡20-21)—የመባረክና የመፈወስ ኃይል (ምሳ. 10፡11፣21) እና ለመርገምና ለማጥፋት ኃይል (ምሳ. 11፡9)።
- ሠ. የዘራነውን እናጭዳለን (ምሳ. 12፡14)።

II. መርሖች ከምሳሌ
- ሀ. አሉታዊና አጥፊ እምቅ ኃይል የሰዎች ንግግር
  1. የክፉ ሰዎች ቃላት (ምሳ. 1፡11-19፤ 10፡6፤ 11፡9፣11፤ 12፡2-6)
  2. የአመንዝራዎች ቃላት (5፡2-5፤ 6፡24-35፤ 7፡5ff፤ 9፡13-18፤ 22፡14)
  3. የሐሰተኛ ቃላት (6፡12-15፣19፤ 10፡18፤ 12፡17-19፣22፤ 14፡5፣25፤ 17፡4፤ 19፡5፣9፣28፤ 21፡28፤ 24፡28፤ 25፡18፤ 26፡23-28)
  4. የሰነፍ ቃላት (10፡10፣14፤ 14፡3፤ 15፡14፤ 18፡6-8)
  5. የሐሰተኛ ምስክር ቃላት (6፡19፤ 12፡17፤ 19፡5፣9፣28፤ 21፡28፤ 24፡28፤ 25፡18)
  6. የሐሜተኛ ቃላት (6፡14፣19፤ 11፡13፤ 16፡27-28፤ 20፡19፤ 25፡23፤ 26፡20)
  7. በችኮላ የሚነገሩ ቃላት (6፡1-5፤ 12፡18፤ 20፡25፤ 29፡20)
  8. የቁልምጫ ቃላት (29፡5)
  9. እጅግ የበዙ ቃላት (10፡14፣19፣23፤ 11፡13፤ 13፡3፣16፤ 14፡23፤ 15፡2፤ 17፡27-28፤ 18፡2፤ 21፡23፤ 29፡20)
  10. የብልግና ቃላት (17፡20፤ 19፡1)
- ለ. አዎንታዊ፣ ፈዋሽና የሚያንጽ እምቅ ኃይል የሰዎች ንግግር
  1. የጻድቅ ቃላት (ምሳ. 10፡11፣20-21፣31-32፤ 12፡14፤ 13፡2፤ 15፡23፤ 16፡13፤ 18፡20)
  2. የመልካም አስተያየት ቃላት (10፡13፤ 11፡12)
  3. የእውቀት ቃላት (15፡1፣4፣7፣8፤ 20፡15)

4. የፈውስ ቃላት (15:4)
5. የመልካም ምላሽ ቃላት (15:1፣4፣18፣23፤ 16:1፤ 25:15)
6. የአስደሳች ምላሽ ቃላት (12:25፤ 15:26፣30፤ 16:24)
7. የሕግ ቃላት (22:17-21)

III. የብኪ አካሄድ (ፈርጅ) በአኪ ቀጥሏል
ሀ. የሰው ንግግር ከሌሎች ሰዎች ጋር እንድንግባባ ያደርገናል፣ ስለ ሕይወት ምን እንደሚሰማን በመግለጽ። ስለዚህ፣ እሱ በርግጥ ማን እንደሆንን ይገልጣል (ማቴ. 12:33-37፤ 15:1-20፤ ማርቆስ 7:2-23)።
ለ. እኛ ማኅበራዊ ፍጥረቶች ነን። እኛ ለመቀበልና ለማጽናት የሚገደን ነን። እሱንም ከእግዚአብሔር እና ከሰዎች ባልንጀሮቻችን እንሻዋለን። ቃላት እነዚህን መሻቶች ለማሳካት ኃይል አላቸው፣ በሁለቱም በአዎንታዊ (2 ጢሞ. 3፡15-17) እና በአሉታዊ (ያዕቆብ 3፡2-12) መንገዶች።
ሐ. በሰዎች ንግግር ብርቱ ኃይል አለ፤ የመባረክ ኃይል (ኤፌ. 4፡29) እና የመርገም ኃይል (ያዕቆብ 3:9)። እኛ ለምንናገረው ኃላፊነት አለብን (ማቴ. 12:36-37፤ ያዕቆብ 3:2-12)።
መ. በቃላችን ይፈረድብናል (ማቴ. 12:33-37፤ ሉቃስ 6:39-45) ብሎም በድርጊታችን (ማቴ. 25:31-46)። የዘራነውን እናጭዳለን (ገላ. 6:7)።

**52፡3** እነዚህ አስደንጋጭ ትይዩ የቅኔ ስንኞች ናቸው። በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠሩት ሰዎች ምን ያህል እንደወደቁ አስቡ! እነርሱ ፍጹም ተቃራኒ ሆነዋል፣ መሆን ከነበረባቸው አቋም!

"ፍቅር" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 12 ሁለቴ በአስደንጋጭ መንገዶች ጥቅም ላይ ውሏል።
1. እነርሱ ክፉን ይወዳሉ ከመልካም ይልቅ፣ ቁ. 3
2. እነርሱ አጥፊ ቃላትን ሁሉ ይወዳሉ፣ ቁ. 4

⊡

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"መልካም የሆነውን ከመናገር ይልቅ"** |
| **አኪጀት** | **"ጽድቅን ከመናገር ይልቅ"** |
| **አየተመት** | **"እውነትን ከመናገር ይልቅ"** |
| **አእቅ** | **"ከእውነት ይልቅ"** |
| **አኢመቅ** | **"ከጽድቅ"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"በእውነተኝነት ከመናገር"** |
| **የተእመቅ** | **"ከእውነተኛ ንግግር ይልቅ"** |
| **LXX** | **"ፍርድን ከመናገር ይልቅ"** |

ይህን ያህል ልዩነት በትርጉሞች ላይ የመኖሩ ምክንያት፣ ይህ ያልተለመደ የ "ጽድቅ" አጠቃቀም በመሆኑ ነው (ቢዲቢ 841)። እሱም ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው "ትክክል" በሚለው መልኩ ሲሆን (መዝ. 23፡3) እዚህ "እውነት" በሚለው መልኩ ነው (መዝ. 58፡1)።

**52፡4 "የሚያጠፋ"** ይህ ስም (ቢዲቢ 118 I) በመሠረቱ ፍችው መዋጥ ነው፣ እናም ለጥፋት ምስያነት ጥቅም ላይ ውሏል።

## መዝሙር ፡ 52፡5-7

**5 ስለዚህ እግዚአብሔር ለዘላለም ያፈርስሃል**
**ከቤትህም ይነቅልሃል ያፈልስሃልም፥**
**ሥርህንም ከሕያዋን ምድር።**
**6 ጻድቃን አይተው ይፈራሉ**
**በእርሱም ይሥቃሉ እንዲህም ይላሉ።**
**7 እግዚአብሔርን ረዳቱ ያላደረገ፥**
**በባለጠግነቱም ብዛት የታመነ፥**
**በከንቱ ነገርም የበረታ ያ ሰው እነሆ።**

**52፡5-7** ይህ አንጓ እግዚአብሔር በክፉ ላይ የሚያደርገውንና የጻድቅን ምላሽ ያቃርናል።
1. የእግዚአብሔር ድርጊት በክፉዎች ላይ ውጤቱ ሞታቸው ነው።
   ሀ. ይሰብራቸዋል ("ያፈርሳል") ለዘላለም – ቢዲቢ 683፣ ኬቢ 736፣ ቃል ያልተጠናቀቀ
   ለ. ይነጥቃል – ቢዲቢ 367፣ ኬቢ 363፣ ቃል ያልተጠናቀቀ፤ ይህ የአልፎ አልፎ ቃልነቱ እዚህ መዝሙርጋ ብቻ ነው፣ ነገር ግን ሌሎች ሦስት መከሰቻዎቹ የሚጠቅሱት "ወደ አንዱ የተወሰደ እሳት" ነው፣ ምሳ. 6:27፤ 25:22፤ ኢሳ. 30:14)
   ሐ. ከቤትህም ያፈልስሃል – ቢዲቢ 650፣ ኬቢ 702፣ ቃል ያልተጠናቀቀ
   መ. ከሕያዋን ምድር ይነቅላቸዋል – ቢዲቢ 1057፣ ኬቢ 1658፣ ፔል የተጠናቀቀ በዋው
2. የጻድቅ ምላሽ በእግዚአብሔር የፍርድ ድርጊት፡
   ሀ. ያያሉ – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ ቃል ያልተጠናቀቀ
   ለ. ይፈራሉ (ማለትም፣ በፍርሃት ንስሐ ይገባሉ) – ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ ቃል ያልተጠናቀቀ

ሐ. በፍርዳቸውም ላይ ይስቅባቸዋል – ቢዲቢ 965፣ ኬቢ 1315፣ ቃል ያልተጠናቀቀ፤ እግዚአብሔር ይስቅባቸዋል፣ መዝ. 2:40 ላይ፤ 37:13፤ ሰውኛ የሆነው ጥበብ ይስቃል፣ ምሳ. 1:26፤ እዚህ ጻድቅ ይስቃል፣ የእግዚአብሔር ፍርድ እሱን በናቁት እና እነርሱን ባሳደዷቸው ላይ ሲወድቅ። እነርሱ "የሳቁት" "የዘሩትን በማጨዳቸው" ስሜት ነው። ፍትሕ ኢፍትሕን ያሸንፋል!

**52፡5** ይህ ምናባዊ ምስያ "ከቤትህም ያፈልስሃል" የሚዛመደው ከእስራኤል የምድረ-በዳ የዘላንነት የድንኳን ሕይወት ቀናት ነው (ዘላንነት እና ኋላም ዘጸአት)። ይኸው ተመሳሳይ ምናባዊ ምስያ ሊታይ ይችላል

1. ሳኦል – 1 ሳሙ. 13:2 (ማለትም፣ ወደ ቤቶቻችሁ)
2. ሼባ – 2 ሳሙ. 20:1 (ማለትም፣ ወደ ቤቶቻችሁ)
3. ይሮብአም I – 1 ነገ. 12:16፤ 2 ዜና. 10:16 (ማለትም፣ ወደ ገዛ አገራችን)
4. ጳውሎስ – 2 ቆሮ. 5:1-10 (ድንኳን በዘይቤነት ለሰው አካል)

▣ **"ዘላለም"** የ"ዘላለም" ጽንሰ ሐሳብ በመዝሙሩ ሦስት ስንኞች ላይ ተገልጿል።

1. የእግዚአብሔር ፍርድ "ለዘላለም" ነው ቁ. 5 (ቢዲቢ 664፣ ኢዮብ 4:20፤ 14:20፤ 20:7፤ 23:7፤ መዝ. 9:7)
2. የእግዚአብሔር በረከት "ለዓለምና ለዘላለም ነው፣" 52:8
   ሀ. ዘላለም – ቢዲቢ 761 (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9:5 ላይ)
   ለ. እስከ – ቢዲቢ 723 I (የሁለቱ ድብልቅ መዝ. 9:5፤ 10:16፤ 21:4፤ 45:6፣17፤ 48:14፤ 104:5፤ 119:44፤ 145:1፣2፣21 ላይ)
3. የታማኝ ተከታዮች ምስጋና ማቅረብ ለ "ዘላለም" ነው ቁ. 9 – ቢዲቢ 761

▣ **"የሕያዋን ምድር"** ይህ አወቃቀር (ቢዲቢ 75፣ ቢዲቢ 313) የሕይወት ፈሊጥ ነው (ኢዮብ 28:13፤ መዝ. 27:13፤ 116:9፤ 142:5፤ ኢሳ. 38:11፤ ኤር. 11:19)። እሱም "የሙታን ምድር" ተቃራኒ ነው፣ ማለትም ሲኦል ወይም ጥልቁ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:6 ላይ)።

▣ **"ሴላህ"** መዝሙር 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻና መግቢያ ለመዝሙር፣ VII ተመልከት።

**52፡7** ቁጥር 7 የሰው መግለጫ ነው፣ ቁጥር 1-4 ላይ የተመለከተው።

1. እሱ እግዚአብሔርን መጠጊያው አላደረገም
2. እሱ በሀብቱ ብዛት ተመክቷል፣ ኢዮብ 31:24-28፤ መዝ. 49:6-9፤ ምሳ. 11:28
3. እሱ በክፉ መሻቱ ብርቱ ነበር

**መዝሙር ፡ 52፡8-9**

**8 እኔስ በእግዚአብሔር ቤት እንደ ለመለመ እንደ ወይራ ዛፍ ነኝ**
**ለዓለምና ለዘላለም በእግዚአብሔር ምሕረት ታመንሁ።**
**9 አድርገህልኛልና ለዘላለም አመሰግንሃለሁ፥**
**በቅዱሳንህም ዘንድ መልካም ነውና ስምህን ተስፋ አደርጋለሁ።**

**52፡8-9** ቁጥር 7 የክፉ ሰውን ባሕርይ እንደሚያሳይ (ማለትም፣ የሚነቀል)፣ ቁጥር 8 የጻድቅ ሰውን ባሕርይ ያሳያል (ማለትም፣ የተተከለ)።

1. እሱ እንደ ለመለመ የወይራ ዛፍ ነው በእግዚአብሔር ቤት መዝ. 1:3፤ 92:12-14፤ 128:3፤ ኤር. 11:16፤ 17:5-8።
2. እሱ በእግዚአብሔር የዘላለም ቸርነት ያምናል፣ መዝ. 13፡5፤ ይህም ቸርነት ዘላለማዊ ነው፣ ዝከ. 52፡16፤ ኃጢአተኞች በራሳቸው ብልጥግና "ይታመናሉ"።
3. እሱ ለእግዚአብሔር ለዘላለም ምስጋና ያቀርባል – ቢዲቢ 392. ኬቢ 389፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ።
4. እሱ በእርሱ ስም ይጠብቃል – ቢዲቢ 875፣ ኬቢ 1082፣ ፔል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ።

**52፡9 "ስምህ"** እሱም ባሕርዩ "መልካም ነው" ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡11-12።

▣ **"በቅዱሳንህም ዘንድ"** ይህ የሚያመለክተው

1. መላእክት
2. ታማኝ ተከታዮች፣ በመቅደስ (ዝከ. ቁ. 8፣ "የእግዚአብሔር ቤት")

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ስለዚህ መዝሙር ያልተለመደው ምንድነው?

2. ኃጢአተኛን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን የተለያዩ የስም አመልካቾች ዘርዝር።
3. እግዚአብሔር በኃጢአተኞች አልያም በጻድቃን ላይ የሚያደርገውን አነጻጽር፣ ቁጥር 5-6።
4. ኃጢአተኞች ምን አደረጉ፣ ከእግዚአብሔር የሚነጥላቸውን?
5. “ቅዱሳን” እነማናቸው፣ የቁጥር 9?

# መዝሙር 53*
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሰነፍ እና ኃጢአተኝነት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ። እንደ ማህላት። የዳዊት ትምህርት። | የአምላክ የለሽ ስንፍና እና የእስራኤል መመለስ | የባለጌ እና የኃጢአተኛ ዘመን መኮነኑ | የሰው ኃጢአተኝነት | የአምላክ የለሽ ዕጣ-ፈንታ |
| 53:1-3 | | | | |
| | 53:1 | 53:1 | 53:1 | 53:1 |
| | 53:2-3 | 53:2 | 53:2-3 | 53:2 |
| 53:4-6 | | 53:3 | | 53:3 |
| | 53:4-5 | 53:4 | 53:4 | 53:4 |
| | | 53:5 | 53:5 | 53:5 |
| | 53:6 | 53:6 | 53:6 | 53:6 |

*ይህ መዝሙር ባመዣኙ የመዝሙር 14 የራሱ ቅጅ ነው፣ ያህዌ ወደ ኤሎሂም ከመቀየሩ በቀር። እዚያ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 53፡1-3**
**ለመዘምራን አለቃ በማኸላት የዳዊት ትምህርት።**
**1ሰነፍ በልቡ። አምላክ የለም ይላል።**
**ረከሱ በበደላቸውም ጐሰቈሉ**
**በጎ ነገርን የሚያደርጋት የለም።**
**2የሚያስተውል**
**እግዚአብሔርንም የሚፈልግ እንዳለ**
**ያይ ዘንድ እግዚአብሔር ከሰማይ የሰው ልጆችን ተመለከተ።**
**3ሁሉ በደሉ፥ አብረውም ረከሱ**
**አንድ ስንኳ በጎን ነገር የሚያደርጋት የለም።**

**መዝሙር ፡ 53፡4-6**
**4ሕዝቤን እንጀራ እንደሚበላ የሚበሉ**
**ግፍ አድራጊዎች ሁሉ አያውቁምን?**
**እግዚአብሔርንም አይጠሩትም።**
**5እግዚአብሔር የግብዞችን አጥንቶች በትኖአልና።**

**በዚያ የሚያስፈራ ሳይኖር እጅግ ፈሩ**
**እግዚአብሔር ንቆአቸዋልና አሳፈርሃቸው።**
**6መድኃኒትን ከጽዮን ለእስራኤል ማን በሰጠ!**
**እግዚአብሔር የሕዝቡን ምርኮ በመለሰ ጊዜ፥**
**ያዕቆብ ደስ ይለዋል እስራኤልም ሐሤት ያደርጋል።**

ይህ መዝሙር ባመዛኙ የመዝሙር 14 የራሱ ቅጅ ነው፣ "ያህዌ" ወደ "ኤሎሂም" ከመቀየሩ በቀር። እዚያ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

# መዝሙር 54
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጠላቶችን ለመከላከል ጸሎት<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ በበገናዎች የዳዊት ትምህርት፣ ዚፋውያን መጥተው ለሳኦል፣ "እነሆ ዳዊት ከእኛ ዘንድ ተሸሽጓል" ባሉት ጊዜ | የተመለሰ ጸሎት ከጠላቶች ስለመታደግ | ከግል ጠላቶች ስለመታደግ ጸሎት | ከጠላቶች ስለመጠበቅ ጸሎት | ወደ አምላክ መጸለይ፣ ወደ ጻድቅ ፈራጅ |
| 54:1-3 | 54:1-3 | 54:1-2 | 54:1-3 | 54:1-2 |
| | | 54:3 | | 54:3 |
| 54:4-5 | 54:4-5 | 54:4-5 | 54:4-5 | 54:4-5 |
| 54:6-7 | 54:6-7 | 54:6-7 | 54:6-7 | 54:6-7 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 54፡1-3**

**1አቤቱ፥ በስምህ አድነኝ፥**
**በኃይልህም ፍረድልኝ።**
**2አቤቱ፥ ጸሎቴን ስማኝ፥**
**የአፌንም ቃል አድምጥ**
**3እንግዶች ቈመውብኛልና፥**
**ኃያላንም ነፍሴን ሸተዋታልና።**
**እግዚአብሔርን በፊታቸው አላደረጉትም። ሴላህ**

**54፡1-3** ይህ አንጓ የሚያሳየው ታሪካዊ መቼት፣ እንደ አንደኛው አካላዊ ጥቃት ነው፣ በአጠቃላይ በሌሎቹ የኪዳኑ ሰዎች። የጸሎት ጥያቄዎቹን ተገንዘብ።

1. አድነኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 446፣ ኬ.ቢ. 448፣ ሂፊል ተተኳሪ
2. ፍረድልኝ (ማለትም፣ በጽድቅ ፍረድልኝ) – ቢ.ዲ.ቢ. 192፣ ኬ.ቢ. 220፣ ቃል ያልተጠናቀቀ ጥቅም ላይ የዋለውም በሦስት ተተኳሪዎች መካከልና ከአንደኛው ጋር ትይዩ ሆኖ ነው። እሱም የሚሠራው እንደ ተተኳሪ ጥያቄዎች ነው፣ ከውጋሪቲካዊ ቅኔ በኋላ (ኤ.ቢ. ገጽ 24)። እሱም "ሕጋዊ ጭብጦችን" ይገልጻል። መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይጠይቃል፣ ፍትሐዊ ውሳኔ። እሱ ያላግባብ ተከሷል
3. ጸሎቴን ስማ – ቢ.ዲ.ቢ. 1033፣ ኬ.ቢ. 1570፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 17:6
4. አድምጥ – ቢ.ዲ.ቢ. 24፣ ኬ.ቢ. 27፣ ሂፊል ተተኳሪ በተመሳሳይ ትይዩ ግንኙነት፣ ከቁ. 3 ጋር መዝ. 5:1፤ 55:1፤ 86:7

▣ **"አምላክ ሆይ"** ይህ የእግዚአብሔር ስም ነው (ኤሎሂም) እሱን የሚጠቅስ እንደ ፈጣሪ፣ ተንከባካቢ፣ እና መጋቢ፣ ለሕይወት ሁሉ፣ በዚህ ምድር ላይ (ዘፍ. 1:6፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 1:1 ላይ)። ሁለቴ ይከሰታል፣ 54:1ሀ እና 54:2ሀ። እሱም ትይዩ ነው፣ በ

1. ስምህ (ልዩ ርዕስ መዝ. 5፡11-12)
2. ኃይልህ፣ 2 ዜና. 20፡6

**54፡2** የመዝሙረኛው ጠላቶች/ተቃዋሚዎች እዚህ ቁጥር ላይ ተገልጸዋል።

1. እንግዶች (ቢ.ዲ.ቢ. 266 I፣ መዝ. 44:20፤ 109:11) ተነሥተውብኛልና፣ 54:3ሀ። ይህ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለሌሎች የኪዳን ሕዝቦች ነው።
2. ኃያላን ሰዎች (ቢ.ዲ.ቢ. 792)። ይህም ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለጠላቶች ነው፣ ለሌሎች ሕዝቦች (ማለትም፣ ወራሪዎች፣ ኢሳ. 13:11፤ ሕዝ. 28:7፤ 30:11፤ 31:12፤ 32:12)
3. እግዚአብሔርን በፊታቸው አላደረጉትም፤ ይህም ሊጠቅስ የሚችለው
   ሀ. አምላክ-የለሽ እስራኤላውያንን፣ መዝ. 14:1፤ 36:1-4፤ 53:1
   ለ. አሕዛብ (ማለትም፣ ብሔራዊ ጠላቶች)
4. ቁ. 5 ላይ እነርሱን "አድብተው የሚጠብቁኝ" በማለት ይገልጻቸዋል (ማለትም፣ ለግድያ)

▣ **"ሴላህ"** መዝሙር 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻና መግቢያ ለመዝሙር VII ተመልከት።

## መዝሙር ፡ 54፡4-5

**[4]እነሆ፥ እግዚአብሔር ይረዳኛል፥**
**ጌታዬም ለነፍሴ ደጋፊዋ ነው።**
**[5]ክፋትን ወደ ጠላቶቼ ይመልሳታል**
**በእውነትህም አጥፋቸው።**

**54፡4-5** መዝሙረኛው ጠላቶቹን ቁ. 3 ላይ እንደ ገለጸ፣ ቁ. 4-5 ላይ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ገልጾ በጠላቶቹ ላይ እንዲነሣ ይጠይቃል።

1. እግዚአብሔር ረዳቴ ነው – ቢ.ዲ.ቢ. 740፣ ኬቢ. 810፣ *ቃል አንቀጽ*፣ መዝ. 27:9፤ 30:10፤ 37:40፤ 118:7
2. ጌታ (*አዶ'ኒ* ቢ.ዲ.ቢ. 10) የነፍሴ ደጋፊዋ ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 701፣ ኬቢ. 759፣ *ቃል አንቀጽ*፣ መዝ. 37:17፣24፤ 41:12፤ 51:12፤ 71:6፤ 145:14)
3. ያመጣል (ይመልሳል፣ ቢ.ዲ.ቢ. 996፣ ኬቢ. 1427)። ኤምቲ *ቃል* ያልተጠናቀቀ አለው በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ነገር የማሶረቲክ ሊቃውንት የሚሉት፣ እሱ የሚነበበው (ቄሬ) እንደ ሂፊል ያልተጠናቀቀ ነው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ።
4. መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይጠይቃል እንዲያጠፋ ("ዝም አሰኛቸው፣" ቢ.ዲ.ቢ. 856፣ ኬቢ. 1035፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 143:12) የእርሱን ጠላቶች፣ እሱን ዝም ለማሰኘት እንደሚሞክሩ መዝ. 18:4፤ 69:4፤ 73:27፤ 94:23፤ 101:5፣8

**54:5**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አየተመት** | **"በታማኝነትህ"** |
| **አኪጀት፣ LXX** | **"በእውነትህ"** |
| **አእቅ** | **"ታማኝ ስለ ሆነ"** |
| **አኢመቅ** | **"በማይለወጥነትህ"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"በታማኝነትህ"** |
| **የተእመቅ** | **"ታማኝነትህን ለማሳየት"** |

ኤምቲ "ታማኝነት" የሚል አለው (ቢ.ዲ.ቢ. 54፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 12:1 ላይ)። እሱም ወደ ኋላ ተመልሶ ከመዝሙረኛው ማስረገጫ ጋር የሚያያዝ ይመስላል፣ ስለ እግዚአብሔር፣ ቁጥር 4 ላይ።

## መዝሙር ፡ 54፡6-7

**[6]ከፈቃዴ እሠዋልሃለሁ አቤቱ፥**
**መልካም ነውና ስምህን አመሰግናለሁ**
**[7]ከመከራ ሁሉ አድኖኛልና፥**
**ዓይኔም በጠላቶቼ ላይ አይታለችና።**

**54፡6** ይህ የመዝጊያ አንጓ (54፡6-7) የሚገልጸው የመዝሙረኛውን መተማመን ነው፣ እግዚአብሔር (ያህዌ፣ ቁ. 6) ለእርሱ እንደሚሠራ። በሚያደርግበት ጊዜ ከዚያም መዝሙረኛው

1. ላንተ መሥዋዕት ያቀርባል – ቢ.ዲ.ቢ. 256፣ ኬቢ. 261፣ *ቃል ተጓዳኝ*
2. ለስምህ ምስጋና ያቀርባል – ቢ.ዲ.ቢ. 392፣ ኬቢ. 389፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ፣ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፤ "ስሙም" መልካም ነው፣ ወይም ለያህዌ ምስጋና ማቅረብ መልካም ነው፣ መዝ. 92:1።

መዝሙር 54፡6 ያልፎ አልፎ አጠቃቀም ነው ያለው፣ ለእስራኤል አምላክ የኪዳን ስም፣ ለያህዌ፣ መጽሐፍ 2 መዝሙር ላይ።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በፍቃደኝነት"** |
| **አኪጀት፣ የተእመቅ** | **"በነጻነት"** |
| **አየተመት** | **"በነጻ ፍቃድ መሥዋዕት"** |
| **አእቅ፣ አኢመቅ** | **"በደስታ"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"የነጻ ፍቃድ መሥዋዕት"** |

ኤምቲ መስተጻምርና ስም አለው (ቢዲቢ 621)። እሱም ሊያመለክት የሚችለው

1. ፍቃደኝነት
2. የነጻ ፍቃድ *መሥዋዕት*

እዚህ ቁ. 1 በተሻለ ይሰማማል።

**54፥7 "እሱ"** ኤምቲ "እሱ" የሚል አለው፣ እሱም ከ "ከስምህ" ጋር የሚዛመድ፣ ቁጥር 6 (ጄፒኤስኦኤ)።

*መዝሙረኛው "መታደግ"* ብቻ አይደለም የሚሆንለት (ቢዲቢ 664፣ KIB 717፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ) ነገር ግን *"ያያል"* (ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) የጠላቶቹን ሽንፈት (መዝ. 59:10፤ 92:11፤ 112:8፤ 118:7፤ ይህም ከባህል አኳያ "በእሱ ላይ ከመሳቅ" ጋር ተመሳሳይ ነው መዝ. 52:6)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "ፍረድልኝ" የሚለው ቃል ምን ማለት ነው?
2. ቁጥር 3 እና 5 ላይ የተጠቀሱት ጠላቶች እነማናቸው?
3. የ "ስም" ን ጠቀሜታ አብራራ፣ (ቁ. 1፣6)።

# መዝሙር 55
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ከሀዲ እንዲጠፉ መጸለይ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ በበገናዎች። የዳዊት ትምህርት | በእግዚአብሔር መታመን፣ ከሀዲ ጓደኛን በተመለከተ | ከግል ጠላቶች የመታደግ ጸሎት | በጓደኛው የተካደ ሰው ጸሎት | ስም ሲጠፋ ጸሎት |
| 55:1-3 | | | | |
| | 55:1-3 | 55:1-3 | 55:1-3 | 55:1-2ለ |
| 55:4-8 | | | | 55:2c-3 |
| | 55:4-8 | 55:4-8 | 55:4-9ሀ | 55:4-5 |
| | | | | 55:6-7 |
| 55:9-11 | | | | 55:8-9ለ |
| | 55:9-11 | 55:9-11 | 55:9ለ-11 | 55:9ሐ-10ሀ |
| 55:12-15 | | | | 55:10b-11 |
| | 55:12-14 | 55:12-15 | 55:12-15 | 55:12 |
| | | | | 55:13-14ለ |
| | | | | 55:14ሐ-15 |
| 55:16-21 | 55:15 | | | |
| | 55:16-19 | 55:16-19 | 55:16-19 | 55:16-17ለ |
| | | | | 55:17c-18 |
| | | | | 55:19 |
| 55:22-23 | 55:20-21 | 55:20-21 | 55:20-21 | 55:20-21 |
| | 55:22 | 55:22 | 55:22 | 55:22 |
| | 55:23 | 55:23 | 55:23 | 55:23ሀ-ለ |
| | | | | 55:23ሐ |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 55፥1-3**
**ለመዘምራን አለቃ በበገናዎች የዳዊት ትምህርት።**
**1አቤቱ፥ ጸሎቴን አድምጥ፥**
**ልመናዬንም ቸል አትበል።**

[2]ተመልከተኝ ስማኝም።
በኀዘኔ ተቅበዘበዝሁ ተናወጥሁም
[3]ከጠላት ድምፅ
ከዓመፀኛም ግፍ የተነሣ
ዓመፃን በላዬ ጥለውብኛልና፥
በቁጣም ጠልተውኛልና።

**55፡1-3** ይህ፣ እንደ ብዙዎቹ ሌሎች መዝሙራት፣ በዚህ ክፍል ውስጥ፣ ስለ ግል ጥቃቶች ይናገራል። ይህ መዝሙር በተለይ የሚያሳምም ነው፣ ምክንያቱም አጥቂዎቹ ባልንጀሮች በመሆናቸው (ዝከ. ቁ. 12-14)።

በርካታ ተተኳሪ ጥያቄዎች አሉ፣ አንድ ተጽዕኗዊ፣ እና ሁለት ተጓዳኞች።

1. አድምጥ – ቢዲቢ 24፣ ኬቢ 27፣ *ሂፊልተተኳሪ፣ መዝ.* 5:1፤ 17:1፤ 39:12፤ 49:1፤ 54:2፣ etc.
2. ራስህን አትሰውር – ቢዲቢ 761፣ ኬቢ 834፣ *ሂዝፔል ያልተጠናቀቀበተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ.* 10:1፤ ሰቆ. 3:56
3. ተመልከተኝም – ቢዲቢ 904፣ ኬቢ 1151፣ *ሂፊልተተኳሪ፣ መዝ.* 5:2፤ 10:17፤ 17:1፤ 61:1፤ 86:6፤ 142:6
4. መልስልኝ – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ *ቃል ተተኳሪ፣ መዝ.* 4:1፤ 13:3፤ 17:6፤ 38:15፤ 60:5፤ 69:13፣16፣17፤ 86:1፣ ወዘተ.
5. ዕረፍት የለኝምና – ቢዲቢ 923፤ ኬቢ 1194፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
   ሀ. ያልፎ አልፎ ቃል፣ አራት ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ፣እዚህጋ ብቻ በጥበብ ሥነ-ጽሑፍ፤ ትርጉሙም ርግጠኝነት የለውም
   ለ. እንዲሁም ደግሞ ይሄንን ቃል መውሰድ ይቻላል፣ እንደ "ቅስቻ፣" መውሰድ ይቻላል ቢዲቢ 242፣ ዝከ. ቁ. 18፤ 42:12፤ 43:5፤ 77:4፤ ጄፒኤስኦኤ
   ሐ. አኪጀት ሁለቱንም አማራጮች ለማደባለቅ ይሞክራል ከ"ማቃሠት ጋር (ቢዲቢ 242) በድምጽ" (ቢዲቢ 223)
6. በርግጥ ተናውጫለሁና ("ድምጽ ያሰማ") – ቢዲቢ 223፣ ኬቢ 242፣ *ሂፊል ተጓዳኝ*፣ LXX

መዝሙረኛው ለዕርዳታ የጮኸበት ምክንያት 55፡4 ላይ ተሰጥቷል።

1. ከጠላቴ ድምጽ የተነሣ
2. ከኃጢአተኞች ግፊት የተነሣ
3. እነርሱ ወድቀውብኛልና (አእቅ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው "ዘንበዋል፣" ነው መዝ. 140፡10) በእኔ ላይ
4. እነርሱም በቁጣ አስገድደው ተነሥተውብኛልና

## መዝሙር ፡ 55፡4-8

[4]ልቤ በላዬ ተናወጠብኝ፥
የሞት ድንጋጤም ወደቀብኝ።
[5]ፍርሃትና እንቅጥቅጥ መጡብኝ፥
ጨለማም ሸፈነኝ።
[6]በርሬ ዐርፍ ዘንድ
እንደ ርግብ ክንፍን ማን በሰጠኝ!
[7]እነሆ፥ ኰብልዬ በራቅሁ
በምድረ በዳም በተቀመጥሁ　　ሴላህ
[8]ከዐውሎና ከብርቱ ንፋስ
ሸሽቼ በፈጠንሁ አልሁ።

**55፡4-8** ይህ አንጓ መዝሙረኛው እንዴት እንደሚሰማው ይገልጻል (ግነታዊ ቋንቋ) ስለ ጠላቶቹ ጥቃት።

1. ልቤ በላዬ ተናወጠብኝ – ቢዲቢ 296፣ ኬቢ 297፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*፣ እሱም ከሞጥ ጋር በተያያዘ ሥቃይ ሥር
2. የሞት ድንጋጤ ወደቀብኝ – ቢዲቢ 956፣ ኬቢ 709፣ *ቃል የተጠናቀቀ*፣ መዝ. 18:4-5፤ 116:3
3. ፍርሃትና እንቅጥቅጥ መጡብኝ – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
4. ድንጋጤም ሸፈነኝ – ቢዲቢ 491፣ ኬቢ 487፣ *ፔል ያልተጠናቀቀ* ከዋው፣ ኢሳ. 21:4፤ ሕዝ. 7:18

ከእነዚህ ፍርሃቶች አኳያ፣ እነርሱን ለማምለጥ ምን ማድረግ እንደሚሻ ይናገራል (ዘይቤአዊ ቋንቋ)።

1. እንደ ርግብ ክንፍ በኖረኝ ("በሰጠኝ") – ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
2. እበርር ዘንድ – ቢዲቢ 733፣ ኬቢ 800፣ *ቃል ተጓዳኝ*
3. ዐርፍ ዘንድ – ቢዲቢ 1014፣ ኬቢ 1496፣ *ቃል ተጓዳኝ*
4. እሸሽ ዘንድ – ቢዲቢ 934፣ ኬቢ 1221፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
5. በምድረ በዳ በተቀመጥሁ – ቢዲቢ 533፣ ኬቢ 529፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
6. ወደ መጠጊያዬ ኮብልዬ በራቅሁ – ቢዲቢ 301፣ ኬቢ 300፣ *ሂፊል ተጓዳኝ*
   ሀ. ዓውሎ ነፋስ – ቢዲቢ 703 (only here)
   ለ. ብርቱ ነፋስ – ቢዲቢ 704

**55፡4 "ልብ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 4፡7 ላይ።

▣ **"የሞት ድንጋጤ"** ሞት ለወደቀው የሰው ልጅ አስፈሪ ነው (መዝ. 18:4-5፤ 116:3)፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ሞትን ይቆጣጠራል፣ ወደ ፍጻሜም ያመጣዋል (ኢሳ. 25:8፤ ሆሴ. 13:14፤ 1 ቆሮ. 15:50-57፤ 2 ጢሞ. 1:10)።

**55፡7 "ሴላህ"** መዝሙር 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻና የመዝሙር መግቢያ VII ተመልከት።

**55፡8 "መጠጊያ ስፍራ"** ስሙ (ቢዲቢ 812) እዚህጋ ብቻ እና መዝሙር 18፡2 ጋ ነው የሚከሰተው።

**መዝሙር ፡ 55፡9-11**

**9 አቤቱ፥ ግፍንና ጠብን በከተማ ውስጥ አይቼአለሁና**
**አስጥማቸው እንደበታቸውንም ቍረጥ።**
**10 በቀንና በሌሊት በቅጥርዋ ይከብቡአታል**
**ዓመፃና ድካም ኃጢአትም በመካከልዋ ነው**
**11 ተንኰልና ሽንገላ**
**ከአደባባይዋ አይርቁም።**

**55፡9-11** ይህ አንጓ የጸሎት ጥያቄውን ይቀጥላል፣ የቁ. 1-2።

1. ይደነጋገሩ ("ይዋጡ፣" ማለትም፣ "ይጥፉ") – ቢዲቢ 118፣ ኬቢ 134፣ ፔል ተተኳሪ፤ ይህ ሥር ጥቅም ላይ የዋለው "መደነጋገር" በሚል መልኩ ነው መዝ. 107፡27፤ ኢሳ. 3፡12፤ 9፡16፤ 19፡3፤ 28፡7
2. አንደበታቸውንም ቁራርጥ – ቢዲቢ 811፣ ኬቢ 928፣ ፔል ተተኳሪ፤ ይህ የዘፍጥረት 11፡1-9 ጠቃሽ ሊሆን ይችላል።

ሁለቱም ቁ. 1 እና ቁ. 2 ጸሎት ናቸው፣ የመዝሙረኛውን ጠላቶች ዕቅድና ተንኮል ለማክሸፍ/ለማስቀረት። ባጠቃላይ እነርሱ በመዝሙረኛው መቀመጫ ከተማ ላይ ችግር ፈጥረው ነበር (ዳዊት ከሆነ፣ እንግዲያውስ ኢየሩሳሌም)። እነርሱ ፖለቲካዊ ጠላቶች ናቸው!

1. ዐመጽን በከተማ ውስጥ አይቻለሁና
2. ጠብን በከተማ ውስጥ አይቻለሁና
3. ቀንና ሌሊት በቅጥርዋ ይከብቧታል
4. ዓመጻ በመካከሏ ነው
5. ተንኮል በመካከሏ ነው
6. ጭቆና ከአደባባዮቿ አይርቅም (ከጎዳናዋ፣ ቢዲቢ 932)
7. ሽንገላ ከጎዳናዎቿ አይርቅም (አደባባይ/የገበያ ስፍራ)

ቁጥር 3፤ 4፤ 5 በማማ ላይ ያለው ጉበኛ (ጠባቂ) ሊሆን ይችላል። በዚህ ጉዳይ ጠባቂዎቹ ሰዎች ተንኮልና ሽንገላ ናቸው!

**መዝሙር ፡ 55፡12-15**

**12 ጠላትስ ቢሰድበኝ፥**
**በታገሥሁ ነበር**
**የሚጠላኝም ራሱን በላዬ ከፍ ከፍ ቢያደርግ፥**
**ከእርሱ በተሸሸግሁ ነበር።**
**13 አንተ ግን፥ እኩያዬ ሰው፥**
**ባልንጀራዬና የልቤ ወዳጅ**
**14 መብልን ከእኔ ጋር በአንድነት ያጣፈጥህ**
**በአንድ ልብ በእግዚአብሔር ቤት ተራመድን።**
**15 ሞት ይምጣባቸው**
**በሕይወት ሳሉ ወደ ሲኦል ይውረዱ**
**ክፋት በማደሪያቸውና በመካከላቸው ነውና።**

**55፡12-15** ይህ አንጓ በመዝሙረኛው ላይ ችግር የፈጠሩት ጓደኞቹ እንደሆኑ ያሳያል።

1. ይህ ጠላት <u>አይደለም</u> የሚሳለቅብኝ — ልሸከመው የምችለው ዓይነት።
2. ይህ የሚጠላኝ <u>አይደለም</u> — ከእርሱ እሸሸግ ዘንድ።
3. እሱም በላዬ ራሱን ከፍ ከፍ ያደረገ <u>አይደለም</u> (መዝ. 35፡26፤ 38፡16፤ ኢዮብ 19፡5) — ከእርሱ እሸሸግ ዘንድ።
4. እሱ ግን አንተ ነህ ሰውየው
   ሀ. እኩያዬ
   ለ. ጓደኛዬ
   ሐ. የቅርብ ባልንጀራዬ
5. መብልን በአንድነት ያጣፈጥን።
6. በአንድ ልብ በእግዚአብሔር ቤት ተራመድን።

መዝሙረኛው ለተንኮላቸው ሐሳቡን ይሰነዝራል።

1. ሞት ይምጣባቸው – ቁሬ፣ ቢዲቢ 674፣ ኬቢ 728፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ወደ ሲኦል ይውረዱ – ቢዲቢ 432፣ ኬቢ 434፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፤ ለሲኦል ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡6 ላይ።
3. ለእነርሱ ፍርድ የመዝሙረኛው ፍላጎት ምክንያት፡
   ሀ. ክፋት በማደሪያ ስፍራቸው (ቢዲቢ 158)
   ለ. ክፋት በመካከላቸው

ቁ.3 ከቁ. 2 ጋር ባግባቡ ትይዩ ስላልሆነ፣ "ማደሪያቸው" ለሚለው ማስተካከያ ለመደረጉ ሐሳብ ተሰንዝሯል።

ሀ. "ወደ መቃብራቸው በፍርሃት ይውረዱ"

ለ. "ወደ ጥልቁ በፍርሃት ይውረዱ" (ማለትም ከምርድ በታች ያለ "መጋዘን")

**55:14**

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

**አየተመት፣ የተእመቅ " ብዙ ሕዝብ"**

**አኢመቅ "ከዚያም በመታወክ ይበርግጉ"**

የዕብራይስጡ ቃል (ቢዲቢ 921) ያልፎ ያልፎ ነው፣ እሱም በብኪ ሦስት ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ።

1. አሕዛብ ተነሣሡ፣ መዝ. 2:1
2. ጫጫታማ፣ የበዓል ስብስብ በቤተ መቅደስ፣ መዝ. 55:14
3. ከፋት የሚሠሩት ሁከት፣ መዝ. 64:2

**መዝሙር ፡ 55፡16-21**

**16 እኔ ግን ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፥**
**እግዚአብሔርም ሰማኝ።**
**17 በማታና በጥዋት በቀትርም እናገራለሁ እጮኽማለሁ፥**
**ቃሌንም ይሰማኛል።**
**18 በእኔ ላይ ብዙ ነበሩና**
**ከሚቃረቡኝ ነፍሴን በሰላም አድናት።**
**19 ቤዛ የላቸውምና፥**
**እግዚአብሔርንም አልፈሩትምና**
**ከጥንት ጀምሮ የነበረ እግዚአብሔር**
**ሰምቶ ያጐሰቍላቸዋል።**
**20 ከእርሱ ጋር ሰላም በነበሩት ላይ እጁን ዘረጋ**
**ኪዳኑንም አረከሱ።**
**21 አፉ ከቅቤ ይልቅ ለዘበ፥ በ**
**ልቡ ግን ሰልፍ ነበረ**
**ቃሎቹም ከዘይት ይልቅ ለሰለሱ፥**
**እነርሱ ግን እንደ ተመዘዘ ሰይፍ ናቸው።**

**55፡16-21** ይህ አንጓ የሚገልጸው እግዚአብሔር ምን እንደሚያደርግ ነው፣ ለ/በ ላይ

1. ለመዝሙረኛው
2. በከሀዲዎቹ ላይ

ቁጥር 19 ሁለቱም መግለጫ ነው፣ የእግዚአብሔር (ማለትም፣ ከጥንት ጀምሮ በዙፋኑ ላይ የተቀመጠው፣ መዝ. 45:6፤ 93:2፤ ሰቆ. 5:19) እና የተቃዋሚዎቹ (ማለትም፣ የማይለወጠው)። መደነጋገሩ የሚነሣው፣ ይህ ሁለተኛ ሐረግ ለእግዚአብሔር ሊሆን በመቻሉ ነው (ማቴ. 3፡6)፣ ነገር ግን እዚህ የሚጠቅሰው የማይለወጠውን የከፋ ልብ ነው፣ የመዝሙረኛውን ጠላቶች።

ቁጥር 16-19ሀ የመዝሙረኛውን ጸሎትና የእግዚአብሔርን ምላሽ ይሰጣል።

1. እግዚአብሔርን እጠራለሁ – ቢዲቢ 894፣ ኬቢ 1128፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ያህዌ ያድነኛል – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ
3. እናገራለሁ – ቢዲቢ 967፣ ኬቢ 1319፣ *ቃል* ተጓዳኝ፣ መዝ. 64:1፤ 142:2፤ ይህ *ሥር* ሊል የሚችለው "ደጅ መጥናት፣" ነው፣ መዝ. 119:15፣23፣27፣148
4. እጮኻለሁ – ቢዲቢ 242፣ ኬቢ 250፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
5. እሱም ድምጼን ይሰማል – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ ከ *ዋው* ጋር
6. እሱ ግን ነፍሴን ከውጊያ ይታደጋታል – ቢዲቢ 804፣ ኬቢ 911፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 19:14 ላይ
7. እግዚአብሔር ይሰማል፣ ቁ. 19a – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ

ቁጥር 19ለ ላይ ለተቃዋሚዎች ምላሽ ይሰጣል ("የሚገባቸውን ስጣቸው" በሚል መልኩ – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፤ ይህ *ሥር* የሚለው "መልስላቸው" ወይም "አውካቸው" ነው። የዘራነውን እናጭዳለን! ቁጥር 19ሐ-21 የእነርሱን ልብና ድርጊት ይገልጻል (የተጠቃለለ "እሱ፣" ዝከ. 55፡18ሐ)።

1. ምንም ለውጥ የለም (*ግሥ* የለውም)
2. እግዚአብሔርን አይፈሩም
3. እጃቸውን ይዘረጋሉ፣ በሰላም ላይ ባሉት ላይ
4. ኪዳኑን ያፈርሳሉ
5. ንግግራቸው የለዘበ ነው፣ በልባቸው ግን ጦርነት አለ
6. የለዘቡ ቃሎቻቸው እንደ ተመዘዙ ሰይፎች ናቸው

ቁ. 2-6 ያሉት ግሦች የተጠናቀቁ ናቸው፣ የጸና የጥላቻና የዓመጻ አዝማሚያን የሚገልጹ።

**55፡17 "በማታና በጠዋት በቀትርም"** ቀን የሚጀምረው በማታ ነው፣ ለጥንት እስራኤላውያን፣ ከዘፍ. 1፡5፣8፣13፣19፣23፣31 የተነሣ። "ቀትር ላይ" የሚያመለክተው ኋለኛ ጊዜን ነው፣ ይሁዲነት ሦስት የጸሎት ጊዜያት ስለሚኖሩት (ዳን. 6፡10)፡

1. በማለዳ መሥዋዕት ጊዜ (3 ሰዓት ጧት)
2. ቀትር
3. በማታ መሥዋዕት ጊዜ (9 ሰዓት ማታ)

እሱም በርግጥ መሆን የሚችለው ሐረጉ "ቀጣይነት" ላለው ዘይቤ ነው።

**55፡19 "ሴላህ"** መዝሙር 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻና መግቢያ ለመዝሙር VII ተመልከት።

***መዝሙር ፡ 55፡22-23***

**[22]ትካዜህን በእግዚአብሔር ላይ ጣል፥ እርሱም ይደግፍሃል**
***ለጻድቁም ለዘላለም ሁከትን አይሰጠውም።***
***[23]አንተ ግን፥ አቤቱ፥ ወደ ሞት ጕድጓድ ታወርዳቸዋለህ***
***የደም ሰዎችና ሸንጋዮች ዘመናቸው ግማሽ አይሞላም***
***እኔ ግን፥ አቤቱ፥ እታመንሃለሁ።***

**55፡22-23** ይህ የመጨረሻ አንጓ ተቃርኗዊ ነው፣ እግዚአብሔር ለታማኝ ተከታይ የሚያደርገው እና ባልታመኑ ጓደኛ(ኞች) ላይ በሚያደርገው።

1. ታማኝ ተከታይ
   ሀ. መዝሙረኛው እንዲጥሉ በብርቱ ያስጠነቅቃቸዋል (ቢዲቢ 1020፣ ኬቢ 1527፣ ሂፊል ተተኳሪ) ሸክማቸውን (ማለትም፣ "ዕጣ፣" ቢዲቢ 396፣ እዚህ*ጋ* ብቻና መዝ. 37፡5) በያህዌ ላይ (1 ጴጥ. 5፡7)
   ለ. የመዝሙረኛውን ምሳሌ መከተል፣ "እኔ በአንተ እታመናለሁ"
2. ያልታመነ ጓደኛ(ኞች)
   ሀ. ወደ ጥፋት ጉድጓድ ያወርዳቸዋል
   ለ. ደም አፍሳሾችና ሐሰተኞች የዕድሜያቸውን እኩሌታ ነው የሚኖሩት

ከታማኝ መታመን የተነሣ፣ ያህዌ ያደርጋል

1. ይደግፋቸዋል – ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 463፣ ፒልፒል ያልተጠናቀቀ፣ ሩት 4፡15፤ ነህ. 9፡21
2. እንዲናወጡ ፈጽሞ አይሰጣቸውም – ቢዲቢ 557፣ መዝ. 125፡1፤ ምሳ. 10፡30

ይህ መዝሙር የሚገልጸው የመካድን ሥቃይና የበርካታ ሌሊቶች ጸሎትን እና አለመበረታታትን፣ ባልታመኑት ወዳጆች ድርጊት እንደሆነ አስታውስ። እነዚህ የመጨረሻ ቁጥሮች ችግር እንደማይኖር የሚገልጹ የተስፋ ቃሎች አይደሉም፣ ነገር ግን የያህዌ መገኘትና ክብካቤ እንጂ። በመጨረሻ ሁሉም ቀና ይሆናል። እኛ የምንኖረው በወደቀው ዓለም ነው፣ ፍትሐዊ ያልሆነና መልካም ያልሆነ ዓለም። አማኞች መከራ ይቀበላሉ፣ በከፋ ሁኔታም ይያዛሉ፣ ነገር ግን ባመዛኙ ወደ ሕይወት ነው፣ ከአፋጣኝ ሁኔታዊ ምላሽ ይልቅ!

አንድ የመጨረሻ አስተያየት፣ በዚህ አንጓ ላይ ማን እንደሚናገር ርግጠኝነት የለም፣ እና ስለዚህ፣ እነርሱ ለማን እንደሚናገሩ።

1. ካህን ወይም ነቢይ መዝሙረኛውን እየሰማ ምላሽ እየሰጠው ይሆናል
2. መዝሙረኛው እየተናገረ ይሆናል
   ሀ. ለራሱ
   ለ. ለአንባቢዎቹ
   ሐ. ለሌሎች በጓደኞቻቸው ለተጎዱ

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ጠላቶች እነማን ናቸው? ድርጊታቸውስ ለመዝሙረኛው ይኼን ያህል ለምን አሠቃይ ሆነ?
2. የመዝሙረኛውን ስሜቶች ግለጽ። (ዝከ. ቁ. 4-8)
3. ቁጥር 9-11 ከዚህ መዝሙር ጋር እንዴት ይገጥማሉ? የተጠቀሰችው ከተማ ማን ናት?
4. ቁጥር 19ን ለመተርጎም ያለው ችግር ምንድነው?
5. ቁጥር 21 የሚናገረው ስለ ምን ዓይነት ሰው እንደሆነ በገዛ ራስህ ቃላት አስቀምጥ።
6. ቁጥር 22-23ን ማን ነው የሚናገረው፣ ለማንስ?
7. ቁጥር 22-23 ላይ ያሉትን የእግዚአብሔርን ድርጊቶች ዘርዝር።

# መዝሙር 56
# የአዲሶቹ ትርጕሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| *ለመታደግ የጸሎት ጥያቄ፣ እና በእግዚአብሔር ላይ በጽኑ መታመን*<br>*ኤምቲ መግቢያ*<br>*ለመዘምራን አለቃ፤ ከቅዱሳን ስለ ራቁ ሕዝብ የዳዊት ቅኔ ፍልስጥኤማውያን በጌት በከበቡት ጊዜ።*<br>56:1-7 | *ከአሠቃዮች እፎይታ ለማግኘት ጸሎት* | *ከግል ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት* | *በእግዚአብሔር ስለመታመን ጸሎት* | *በእግዚአብሔር መታመን* |
| | 56:1-2 | 56:1-4 | 56:1-4 | 56:1-2 |
| | 56:3-4 | | | 56:3-4 |
| | 56:5-7 | 56:5-7 | 56:5-7 | 56:5-6 |
| 56:8-13 | | | | 56:7-9ሀ |
| | 56:8-11 | 56:8-11 | 56:8-11 | |
| | | | | 56:9ለ-11 |
| | 56:12-13 | 56:12-13 | 56:12-13 | 56:12-13 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 56፡1-7**

**1አቤቱ፥ ሰው ረግጦኛልና ማረኝ**
**ሁልጊዜም በሰልፍ አስጨንቆኛል።**
**2የሚዋጉኝ በዝተዋልና**
**ሁልጊዜ ቀኑን ሁሉ ጠላቶቼ ረገጡኝ።**
**3እኔ ግን ፈራሁ**
**በአንተም ታመንሁ።**
**4በእግዚአብሔር ቃሉን አመሰግናለሁ**
**በእግዚአብሔር ታመንሁ፥**
**አልፈራም**
**ሰው ምን ያደርገኛል?**
**5ሁልጊዜ ቃሎቼን ያጸይፉብኛል**
**በእኔ ላይም የሚመክሩት ሁሉ ለክፉ ነው።**
**6ይሸምቁብኛል ይሸሽጉኝማል፥**
**እነርሱም ተረከዜን ይመለካከታሉ፥**
**ሁልጊዜም ነፍሴን ይሸምቁባታል።**
**7በምንም ምን አታድናቸውም**
**አሕዛብን በቍጣ ትጥላቸዋለህ።**

**56፥1-7 *"ማረኝ"*** ይህ ተተኳሪ (ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334) ብዙ መዝሙሮችን ይጀምራል (መዝ. 4፡1፤ 6፡2፤ 51፡1፤ 57፡1 [ሁለቴ]፤ 86፡3፤ 123፡3 [ሁለቴ]) እናም በሌሎች በብዙዎች ላይ ይከሰታል (መዝ. 9፡13፤ 25፡16፤ 26፡11፤ 27፡7፤ 30፡10፤ 31፡9፤ 41፡4፣10፤ 86፡16፤ 119፡29፣58፣132)። እሱም ዘወትር የሚያያዘው

1. ከጠላቶች መታደግ
2. የኃጢአት ይቅርታ

በዚህ መዝሙር ላይ ጸሎቱ በቁ. 1 ምክንያት የተነሣ ነው። መዝሙረኛው ጠላቶቹን እንዴት እንደሚገልጽ ተገንዘብ (ቁ. 1-2)።

1. መርገጥ (ወይም "ማቃሠት፣" ተመሳሳይ ተናባቢ) እሱን፣ ቁ. 2 – ቢዲቢ 983 II፣ ኬቢ 1375፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ዝከ. ቁ. 3፤ መዝ. 57፡3፤ ሕዝ. 36፡3፤ አሞጽ 8፡4
2. እሱን በኩራት ተዋግተውታል፣ ቁ. 2 – ቢዲቢ 535፣ ኬቢ 526፣ *ቃል* አንቀጽ
3. ቃሎቹን ያጣምማሉ ("ይጸየፉሉ" እሱን) ቃሎቹን፣ ቁ. 5 – ቢዲቢ 780፣ ኬቢ 864፣ ፔል ያልተጠናቀቀ
4. ሐሳባቸው በእርሱ ላይ ክፉ ነው፣ ቁ. 5 – ግሥ የለውም
5. ማጥቃት ("ሁከትን ይፈጥራሉ")፣ ቁ. 6 – ቢዲቢ 158፣ ኬቢ 184፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 59፡3፤ 140፡3
6. ይሸምቃሉ ("ይሸሸጋሉ")፣ ቁ. 6 – ኤምቲ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ አለው፣ *ቁሬ ቃል* ያልተጠናቀቀ የቢዲቢ 860፣ ኬቢ 1049
7. ርምጃውን ይመለካከታሉ ("ተረከዞቹን")፣ ቁ. 6 – ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ (ማለትም፣ ስለሆነም የማጥቂያ ጊዜና ስፍራ ለመፈለግ)፣ መዝ. 71፡10
8. ነፍሱን ለመንጠቅ ይሸምቁበታል፣ ቁ. 6 – ቢዲቢ 875፣ ኬቢ 1082፣ ፔል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 119፡95

**56፥1 "ሁልጊዜ"** ይህ ቀጣይነት ያለውን ጥቃት የሚያመለክተው ፈሊጥ ቁጥር 1፣ 2፣ እና 5 ላይ ጥቅም ላይ መዋሉን ተገንዘብ።

መዝሙረኛው ቀኑን ወደፊት እየጠበቀ ነው (ዝከ. ቁ. 3) ጠላቶቹ ወደ ኋላ የሚመለሱበትን፣ ቁ. 9ሀ። በመጽሐፍ ቅዱስ "ቀን" ሊያመለክት የሚችለው

1. ጊዜያዊ ፍርድ
2. ፍጻሜያዊ ፍርድ ነው።

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ያ ቀን መዝ. 11፡4ለ ላይ።

◘

**አአመመቅ ኅዳግ "ተዋጊ ሰዎች"**
**አየተመት "ጠላቶች"**
**አእቅ "ጠላቶች"**
**ጀፒኤስአኤ "ተቀናቃኞች"**
**የተእመቅ "አጥቂዎች"**

ኤምቲ *ቃል* የድርጊት አንቀጽ አለው "መዋጋት" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 535፣ ኬቢ 526)። ይኸው ተመሳሳይ ምድብ "ሰዎች" ተብሎ ይጠራል (ማለትም፣ ደካማ ሰዎች፣ ቢዲቢ 60)።

**56፥2 "በኩራት"** ኤምቲ "ከፍታ" የሚል ስም አለው (ቢዲቢ 928)። እሱም በሁለት መንገዶች ይተረጎማል።

1. የጠላቶች ትዕቢተኝነት፣ አአመመቅ፣ NIV
2. ከፊሉ የእግዚአብሔር መጠሪያ
   ሀ. "ልዑሉ፣" LXX፣ አኪጆት፣ አየተመት፣ የተእመቅ
   ለ. "ኃያል አምላክ፣" አእቅ
   ሐ. "ከፍ ያለው፣" ጀፒኤስአኤ

**56፥3** ቁጥር 3 የተደገመ ጭብጥ ነው፤ ቁጥር 4 እና 11 ላይ የተደገመ።

1. እኔ ግን ፈራሁ – ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
2. በእግዚአብሔር እታመናለሁ – ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 4፡5 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት
3. አልፈራም፣ ቁ. 4፣11፣ መዝ. 112፡7-8፤ 118፡6

**56፥4 "በእግዚአብሔር ቃሉን አመሰግናለሁ"** ይህ ቁጥር 10 ላይ መደገሙን ተገንዘብ፣ ትይዩ በሆነ መንገድ ኤሎሂም እና ያህዌ በሚያያዙበት።

"ቃሉ" (ቢዲቢ 182) ትይዩ ነው ከ"መሐላዎችህ" ጋር (ቢዲቢ 623)፣ ቁ. 12። በርካታ ቃላት አሉ የያህዌን መገለጦች ባሕርይ ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋሉ። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡2 ላይ።

◘ **"ሰው ('ሥጋ') ምን ያደርገኛል"** ይኸው ተመሳሳይ ሐሳብ መዝ. 118፥6 ላይ ተገልጿል፣ እንዲሁም ዕብ. 13፥6 ላይ ተጠቅሷል። ጽንሰ-ሐሳቡም ከመንፈሳዊ ኃይላት ጋር በተያያዘ ሮሜ. 8፥31፣ 35-39 ላይ ተመልክቷል።

**56፥7** ከክፋትና ቀጣይነት ካለው ጥቃት የተነሣ መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይጠይቃል በጠላቶቹ ላይ ፍርድ እንዲያደርግ።

1. ጣላቸው (ስለ ወንጀላቸው፣ የማያመልጡትን፣" አኪጆት) – ቢዲቢ 812፣ ኬቢ 930፣ ፔል ተተኳሪ
   ሀ. የግሡ ፍቺ "አድን፣" መዝ. 17፡13፤ 18፡3፣ እዚህ ጥያቄ መሆን ይኖርበታል ወይም ትርጉሙ አሉታዊ ማካተት ይኖርበታል፣ "ከወንጀል" ጋር ማረሚያ (የተእመቅ፣ LXX)
   ለ. እሱ ደግሞ "ማዳን፣" ቀይሮ ይሆናል ቢዲቢ 812፣ ꙍꙍꙍ ፣ ወደ "መክበድ፣" ቢዲቢ 814፣ ꙍꙍꙍ
2. አሕዛብን መጣል – ቢዲቢ 432፣ ኬቢ 434፣ *ሂፊል* ተተኳሪ፣ መዝ. 55፡23። አስደናቂ የሚሆነው "አሕዛብ፣" ይኸውም ዘወትር ለብሔራዊ ወገኖች ጥቅም ላይ የዋለው (አእመቅ፣ የተእመቅ)፣ እዚህ ጥቅም ላይ ውሏል። በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ።
   ሀ. ይህ ንጉሣዊ መዝሙር ነው፣ ሌሎች ሕዝቦችን የሚጠቅስ

ለ. ይህ እስራኤላዊ/ይሁዳዊ ነው በባዕዳን መካከል የሚኖር
ሐ. ጠላቶቹን የመጥቀሻ መንገድ፣ እንደ ኪዳን-የለሽ ሕዝቦች የሚያደርጉትን

**መዝሙር ፡ 56፡8-13**

**8 አምላክ ሆይ፥ ሕይወቴን ነገርሁህ**
**እንባዬን እንደ ትእዛዝህ**
**በፊትህ አኖርህ።**
**9 በጠራሁህ ጊዜ ጠላቶቼ ወደ ኋላቸው ይመለሳሉ**
**አንተ አምላኬ እንደ ሆንህ እነሆ፥ አወቅሁ።**
**10 በእግዚአብሔር ቃሉን አመሰግናለሁ**
**በእግዚአብሔር ቃሉን አከብራለሁ።**
**11 በእግዚአብሔር ታመንሁ፥**
**አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል?**
**12 አቤቱ፥ የምስጋና ስእለት**
**የምሰጥህ ከእኔ ዘንድ ነው**
**13 ነፍሴን ከሞት፥**
**እግሮቼን ከመውደቅ አድነሃልና፥**
**በሕያዋን ብርሃን**
**እግዚአብሔርን ደስ አሰኘው ዘንድ።**

**56፡8-13** ይህ አንጓ የሚያሳየው የመዝሙረኛውን የእምነት ቁርጠኝነት ነው፣ እግዚአብሔር ከእርሱ ጋርና ለእርሱ በመሆኑ። አንድ ቀን ጠላቶቹ የድርጊታቸውን ውጤት ይጋፈጣሉ (ቁ. 9)።

**56፡8** እግዚአብሔር ያውቃል፣ መዝሙረኛው በምን ውስጥ አልፎ እንደሚሄድ (ዘጸ. 3፡7)። እሱም ይሄንን የእምነት ርዕዮተ-ዓለም ይገልጻል (ማለትም፣ በቅዱስ ቃሉ ተስፋዎች ላይ በመመሥረት) በ

1. *ግሥ*፣ "ይመለከታል" (ማለትም፣ እግዚአብሔር ያውቃል) – ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
2. *ግሡ*፣ "እንባዬን በፊትህ አኖርህ" – ቢዲቢ 962፣ ኬቢ 1321፣ *ቃል ተተኳሪ* (ማለትም፣ የጸሎት ጥያቄ)፤ እሱም ዘይቤ ነው፣ መዝሙረኛው ያለፈበትን መከራና ክፉ ነገር፣ በጠላቶቹ እጅ/ቃል
3. *መጽሐፍህ* — "መጽሐፍ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 707) "ይመለከታል" ከሚለው *ግሥ ጋር* ተመሳሳይ ነው (ቢዲቢ 707)። "መጽሐፍ" መጽሐፍ ቅዱሳዊ ፈሊጥ ነው፣ ለእግዚአብሔር መታሰቢያ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር ሁለቱ መጻሕፍት፣ መዝ. 9፡5 ላይ።

▣ ***"መያዣ"*** ቃሉ (ቢዲቢ 609) ፍችው የእንስሳ ቆዳ ነው (የበግ) ለፈሳሽ መያዣ የተበጀ (ኢያ.9:4፣13፤ መሳ. 4:19፤ 1 ሳሙ. 16:20፤ መዝ. 119:83)።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"መንከራተት"** |
| **አየተመት** | **"መዟዟር"** |
| **አእቅ** | **"መቸገር"** |
| **አኢመቅ** | **"ኀዘን"** |
| **የተእመቅ** | **"ኀዘን"** |

የዕብራይስጡ ስም (ቢዲቢ 627 I) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው። እሱም ተመሳሳይ ተናባቢ ነው እንደ "ወደ እና ከ መንቀሳቀስ" "መንከራተት፣" "መራወጥ" "ኀዘንን ማሳየት" (ቢዲቢ 626)። የ "መንከራተት" አጠቃቀም መዝ. 36:11፤ 59:11፤ 2 ነገ. 21:8 ላይ ይታያል። የድምጽ መቀያየር በዕብራይስጥ አለ፣ በ "መንከራተት" እና "በመያዣ" መካከል።

**56፡9 "በተጣራሁኝ ጊዜ"** "መጣራት" የእምነት መግለጫ ሊሆን ይችላል።

1. ቁ. 9ለ
2. ቁ. 3ሀ
3. ቁ. 4ሀ-ለ

ምንንም ያመልክት፣ እሱ የሚያመለክተው የፍቃደኝነት እምነትን ነው። ሥነ-መለኮታዊ ተቃርኖ አለ፣ በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና በሰው ነጻ ፍቃድ መካከል። ሁለቱም ለኪዳን አስፈላጊ ናቸው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 25፡12 እና መዝ. 25፡10 ላይ።

▣ **"ይሄንን አውቃለሁ፣ እግዚአብሔር ለእኔ እንደሆነ"** ይህ የዕብራይስጡ ቃል "ማወቅ" ፍቺ ተቀያሪ ነው (ቢዲቢ 393)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ መዝ. 1፡6 ላይ።

**56፡12 "መሐላ"** ይህ ሌለኛው መንገድ ነው፣ የእግዚአብሔርን ተስፋ ለመጥቀስ (ዝኪ. ቁ. 10ለ) ወይም መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር የገባውን ቃል የሚያመለክት ይሆናል። አንድ ጊዜ ከተፈጸመ ወዲያ

1. *መሥዋዕት ይጠይቃል* (ዝኪ. ቁ. 12ለ)

2. ቃላዊ ምስጋና ይጠይቃል

ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ሊያመለክት የሚችለው የመዝሙረኛውን የሞት ፍራቻ ነው፣ በጠላቶቹ፣ እናም እግዚአብሔርን ይጠይቃል እንዲያድነው። በዚህ ጥያቄ ላይ የተወሰነ ዓይነት መሐላ ያደርጋል። እግዚአብሔርም አድኖታል፣ እናም ቃለ-መሐላውን መፈጸም ይኖርበታል።

**56፡13** መዝሙረኛው በርካታ ነገሮችን ይጠቅሳል፣ እግዚአብሔር ያደረገለትን።

1. ነፍሱን ከሞት አድኗታል – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ ሂፊል የተጠናቀቀ፤ ይህ መያያዝ የሚኖርበት ከቁጥር 6 ጋር ነው
2. እግሮቹን ከመሰናከል ጠብቋል፣ እናም በእግዚአብሔር ፊት እንዲራመድ ፈቅዶለታል፤ መልካም አኗኗር ንጹሕ እንደሆነ፣ የተስተካከለ፣ ማሰናከያ እንደሌለበት መንገድ/ጎዳና ተገልጿል (መዝ. 1፡1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)። እነርሱ "አካሄዱን ጠብቀዋል" ቁ. 6 ላይ፣ አሁን ግን እግዚአብሔር እንዲራመድ ረድቶታል።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የመዝሙሩ ዋነኛ ነገር ተደጋጋሚ አዝማች አለው፣ ምንድነው እሱ?
2. "የመጽሐፍን" ፈሊጥ አብራራ። ምን ያህል "መጻሕፍት" መጽሐፍ ቅዱስ ይጠቅሳል፣ እግዚአብሔር የሚጠብቃቸው?
3. "በዚያ ቀን" ምን ማለት ነው?
4. ቁጥር 10ን በገዛ ራስህ ቃላት አብራራ።
5. "በእግዚአብሔር ፊት መራመድ" ምን ማለት ነው?

# መዝሙር 57
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ከመከራ ለመጠበቅ ጸሎት | ከጠላቶች ለመጠበቅ ጸሎት | ከግል ጠላቶች ለመጠበቅ ጸሎት | የዕርዳታ ጸሎት | በአስፈሪ ጠላቶች መሐል |
| <u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>ለመዘምራን አለቃ፤ ከሳኦል ፊት ሸሽቶ በዋሻ በነበረበት ጊዜ የዳዊት ቅኔ። | | | | |
| 57:1-3 | | | | |
| | 57:1 | 57:1-3 | 57:1 | 57:1 |
| 57:4-6 | 57:2-3 | | 57:2-3 | 57:2-3 |
| | 57:4-5 | 57:4 | 57:4 | 57:4 |
| | | 57:5 | 57:5 | 57:5-6 |
| 57:7-11 | 57:6 | 57:6-10 | 57:6 | |
| | 57:7-8 | | 57:7-11 | 57:7 |
| | | | | 57:8 |
| | 57:9-10 | | | 57:9-11 |
| | 57:11 | 57:11 | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር ባሕርይ ያደረገው ድርብ (ወይም ሦስትዮሽ) ቃላትን መጠቀም ነው።
1. ራራልኝ፣ ቁ. 1
2. መጠጊያ ሁነኝ፣ ቁ. 1
3. ልቤ ጽኑ ነው፣ ቁ. 7
4. ንቃ፣ ቁ. 8

ለ. ቁጥር 6 እና 7 ላይ በርካታ ግሦች አሉ፣ *ቆፍ* በሚለው የዕብራይስጥ ፊደል የሚጀምሩ።
1. ተዘጋጅ – ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 464
2. አዘንብል – ቢዲቢ 496፣ ኬቢ 493
3. ቆፍር – ቢዲቢ 500፣ ኬቢ 496
4. ውደቅ – ቢዲቢ 656፣ ኬቢ 709
5. ጽኑ – ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 464 (ሁለቴ)

ደግሞም ስሞች
1. ክብር ቁ. 5 – ቢዲቢ 458
2. ነፍሴ/ጉበት፣ ቁ. 8 – ቢዲቢ 458 (አአመመቅ "ክብር፣" የሚል አለው ቢዲቢ 458)
3. መሰንቆ፣ v. 8 – ቢዲቢ 490

ሐ. ቁጥር 6 ሁነኛ "የተገላቢጦሽ" ሐሳብ ነው፣ እሱም በብኪ እጅግ የተለመደ። ጠላቶች ክፉ ያስባሉ ነገር ግን በገዛ ተንኮላቸው ይያዛሉ።

መ. ሁለት ሥነ-መለኮታዊ ቃላት ተደግመዋል።
1. ደግነት (ሄስድ) – ቢ.ዲ.ቢ. 338፣ ዝከ. ቁ. 3 (ሰውኛ ዘይቤ)፣ 10 (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7 ላይ)
2. ታማኝነት/እውነት (ኢሜት) – ቢ.ዲ.ቢ. 54፣ vv. 3 (ሰውኛ ዘይቤ)፣ 10 (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 12:1 ላይ)

ሠ. ይህ መዝሙር "አሕዛብን" ይጠቅሳል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ሁለንተናዊ የመዋጀት ዕቅድ፣ የመዝሙር 2 መግቢያ ላይ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 57፡1-3**

**[1]ማረኝ፥ አቤቱ፥ ማረኝ፥**
**ነፍሴ አንተን ታምናለችና**
**ጉዳት እስኪታልፍ ድረስ**
**በክንፎችህ ጥላ እታመናለሁ።**
**[2]ወደሚረዳኝ እግዚአብሔር**
**ወደ ልዑል እግዚአብሔር እጮኻለሁ።**
**[3]ከሰማይ ልኮ አዳነኝ፥**
**ለረገጡኝም ውርደትን ሰጣቸው ሴላህ**
**እግዚአብሔር ቸርነቱንና እውነቱን ላከ።**

**57፡1** ይህ መዝሙር ባሕርዩ ድርብ የቃላት አጠቃቀም ነው (ማለትም፣ ዕብራይስጥ ትይዩነት፣ የመግቢያ ጽሑፉን በዕብራይስጥ ቅኔ ላይ ተመልከት)። ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ሀ።

◘ **"ማረኝ"** ቁጥር 1 (ሁለቴ)። መዝ. 56፡1 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት።

◘ **"መታመኛ"** ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 340፣ ኬቢ. 334) ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ መዝሙር ላይ። መዝ. 5፡11 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት። እዚህጋ በመካከል መለዋወጥ አለ
1. የተጠናቀቀው የተፈጸመ ድርጊትን ይገልጻል፣ እንዲሁም የውጤት አቋምን
2. ያልተጠናቀቀው በሂደት ላይ ያለውን ቀጣይነት ያለውን ድርጊት ይገልጻል

◘ **"በክንፎችህ ጥላ"** ይህ ከበርካታ አንስታይ (የሴት) ዘይቤዎች አንዱ ነው፣ እግዚአብሔርን የሚገልጽ።
1. እንደ እናቲት ወፍ – ዘፍ. 1:2፤ ዘጸ. 19:4፤ ዘዳ. 32:11፤ 33:12፤ ኢሳ. 31:5
2. እንደ እምታጠባ እናት – ኢሳ. 49:15፤ 66:13፤ ሆሴ. 11:4 (ማሻሻያ)

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጥላ እንደ ዘይቤ ለጥበቃና ለክብካቤ፣ መዝ. 5፡11-12 ላይ።

◘ **"ጉዳት እስኪታልፍ ድረስ"** ይህ ቀጣይነት ያለው ዘይቤ ነው፣ እግዚአብሔር እንደ እናቲት ወፍ። "ጥፋት"ን ተመልከት (ማለትም፣ አጥፊ ነፋስ ወይም ማዕበል፣ ቢ.ዲ.ቢ. 217፣ ከመዝ. 55፡8 ተመሳሳይ ቃላት) ሰውኛ ዘይቤ ሆኗል (ኢሳ. 26፡20)።

**57፡2 "ልዑል እግዚአብሔር"** ይህ ኤሎሂም የሚለው ስም ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 43፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡1 ላይ) ከኤሊኦን ጋር ተደባልቆ (ቢ.ዲ.ቢ. 751 I)። ማስታወሻ ተመልከት 7፡17 ላይ።

◘ **"እግዚአብሔር"** ይህ ኤል ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 42)፣ ለመለኮት አጠቃላይ ስም በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ)።

◘ **"ሁሉንም ነገር የሚያደርግልኝ"** እንዴት ያለው ሁሉንም ነገር የሚያካትት የእምነት ማስረገጫ ነው (መዝ. 138፡8)። ልምድ እንደሚነግረን "ሁሉም" መገለጽና መወሰን ይኖርበታል። ይህ ታማኝ ተከታይ ግን ያምናል (ፊሊ. 1፡6)።

በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የእግዚአብሔር ድርጊቶች ቁጥር 3 ላይ ተመልከተዋል።
1. ከሰማይ ላከ — ማን እና ምን እንደሆነ አልለየም
2. አዳነኝ — ከክፉ ጠላቶች (ዝከ. 57፡4፣6)
3. ለረገጡኝም ውርደትን ሰጣቸው (መዝ. 56፡2) — ቢ.ዲ.ቢ. 357 I፤ ፍችውም "መገሠጽ" ወይም "ማዋረድ" ነው ጎጂ ነገር የሚሉትን (ጠላቶች እንደ ዱር አንበሳ መገለጻቸውን ተመልከት፣ ባለ ሰላ ጥርስ፣ ቁ. 4)
4. እሱም ላከ፣ ሰዋዊ ዘይቤ የሆነውን ቸርነቱን እና እውነቱን/ታማኝነቱን፣ መዝ. 89:14 እና ደግሞ መዝ. 43:3፣ እዚያም "ብርሃን" እና "እውነት" ሰውኛ ዘይቤ የሆኑበት፣ እንደ ያህዌ አገልጋዮች።

**57፡3 "ከሰማይ ላከ"** "ሰማይ" የሚለው ቃል ሁለት የተለዩ አጠቃቀሞች አሉት።
1. ከምድር በላይ ያለው ከባቢ አየር (ዝከ. 57፡5)
2. ያህዌ የሚኖርበት ስፍራ (ዝከ. 57፡5)

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማይ መዝ. 8፡1 ላይ። በብኪ. አስተሳሰብ እግዚአብሔር ከሰው ልምድና መረዳት በላይ ነው። የእስራኤሉ ቅዱስ ከኃጢአተኛው ፍጥረት ተለይቷል፣ ከዘፍጥረት 3 በኋላ። እሱም በቅድስተ ቅዱሳን ከእስራኤል ጋር ይኖራል፣ በኪሩቤል ክንፎች መካከል፣ ከኪዳኑ ታቦት የምሕረት መከደኛ በላይ (እሱም ተምሳሌትነቱ የማስተሠርያ ስፍራ ነው፣ ሌዋውያን 16)። ሆን ተብሎ የተደረገ ተቃርኖ አለ፣ በያህዌ ወሰን የሌለው ቅድስናና ከእስራኤል ጋር ባለው ርምጃ መካከል።

▣ **"ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 3፡2 ላይ እና መግቢያ ለመዝሙር VII ላይ።

**መዝሙር ፡ 57፡4-6**

**4ነፍሴን ከአንበሶች መካከል አዳናት።**
**ደንግጬ ተኛሁ**
**የሰው ልጆች ጥርሳቸው ጦርና ፍላጻ፥**
**አንደበታቸው የተሳለ ሾተል ነው።**
**5አምላክ ሆይ፥ በሰማያት ላይ ከፍ ከፍ በል**
**ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትሁን።**
**6ለእግሮቼ ወጥመድን አዘጋጁ፥**
**ነፍሴንም አጐበጡአት**
**ጉድጓድ በፊቴ ቈፈሩ፥**
**በእርሱም ወደቁ። ሴላህ።**

**57፡4-6** እነዚህ ቁጥሮች ባሕርይ ያደረጉት የመዝሙረኛውን ጠላቶችና የእርሱን አምላክ ነው፣ የሚደግፈውን (ዝከ. ቁ. 2)።

1. ጠላቶች
   ሀ. እንደ አንበሳ
   ለ. እሳት የሚተነፍሱ (ወይም፣ ኬቢ. 521 II፣ ለመስበር፣ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው)
   ሐ. ጥርስ/ቃላት ጦር እና ፍላጻ ናቸው
   መ. እሱን ለመያዝ እና ለመግደል ወጥመድ አዘጋጁ፣ ነገር ግን በእርሱ ላይ ራሳቸው ወደቁ (ምሳ. 26፡27)
2. እግዚአብሔር (ዝከ. ቁ. 5፣11)
   ሀ. ከፍ ያለ ነው – ቢዲቢ. 926፣ ኬቢ. 1202፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ እዚህጋ "ሰማያት" የሚያመለክቱት ከምድር በላይ ያለውን ከባቢ አየር ነው (ትይዩነትን ተመልከት)
   ለ. ክብርህ ከምድር በላይ ነው
3. መዝሙረኛው
   ሀ. እኔ ...በመካከል መጋደም ይኖርብኛል – ቢዲቢ. 1011፣ ኬቢ. 1486፣ *ቃል ተጓዳኝ*
   ለ. ነፍሴ ጎበጠ – ቢዲቢ. 496፣ ኬቢ. 493፣ *ቃል* የተጠናቀቀ

**መዝሙር ፡ 57፡7-11**

**7ልቤ ጨካኝ ነው፥ አቤቱ፥ ልቤ ጨካኝ ነው**
**እቀኛለሁ፥ እዘምራለሁ።**
**8ክብሬ ይነሣ፥**
**በገናና መሰንቆም ይነሡ**
**እኔም ማልጄ እነሣለሁ።**
**9አቤቱ፥ በአሕዛብ ዘንድ አመሰግንሃለሁ፥**
**በወገኖችም ዘንድ እዘምርልሃለሁ**
**10ምሕረትህ እስከ ሰማይ ድረስ ከፍ ብላለችና፥**
**እውነትህም እስከ ደመናት ድረስ።**
**11አምላክ ሆይ፥ በሰማያት ላይ ከፍ ከፍ በል**
**ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትሁን።**

**57፡7-11** ይህ አንጓ ከሞላ ጎደል እንደ መዝ. 108፡2-6 ዓይነት ነው። እሱም የአምልኮ ሥርዓተዊ አዝማች ይኖረዋል።

**57፡7-9** ይህ አንጓ የሚገልጸው የመዝሙረኛውን እምነትና መተማመን ነው፣ በያህዌ ድርጊቶች፣ በእርሱ በኩል።

1. ልቤ ጨካኝ ነው፣ ቁ. 7 (ሁለቴ) – ቢዲቢ. 465፣ ኬቢ. 464፣ *ኒፋል* አንቀጽ
2. እዘምራለሁ፣ ቁ. 7 – ቢዲቢ. 1010፣ ኬቢ. 1479፣ *ቃል ተጓዳኝ*
3. ምስጋና እዘምራለሁ፣ ቁ. 7 – ቢዲቢ. 274፣ ኬቢ. 273፣ *ፔል ተጓዳኝ*
4. ክብሬ ሆይ ተነሥ (ወይም "ነፍሴ፣" "ጉበት፣" ሁለቱም ቢዲቢ. 458)፣ ቁ. 8 – ቢዲቢ. 734፣ ኬቢ. 802፣ *ቃል ተተኳሪ*
5. በገና ተነሥ መሰንቆም (ማለትም፣ የመዝሙረኛው መሣርያዎች ናቸው፣ እግዚአብሔርን የሚያመሰግንባቸው)፣ ቁ. 8 – ቢዲቢ. ተመሳሳይ ግሥ እንደ ቁ. 4
6. እኔም ማልጄ እነሣለሁ፣ ቁ. 8 – ቢዲቢ. 734፣ ኬቢ. 802፣ *ሂፊል ተጓዳኝ*
7. ምስጋና አቀርባለሁ፣ ቁ. 9 – ቢዲቢ. 392፣ ኬቢ. 389፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

8. ምስጋና እዘምራለሁ፣ ቁ. 9 – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ፔል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

**57፡9** በ "ሕዝቦች" (ቢዲቢ 766 I) እና "አሕዛብ" መካከል ያለውን ትይዩነት ተገንዘብ (ቢዲቢ 115 እና ቢዲቢ 52፣ ማለትም፣ የኪዳን ሕዝቦች ያልሆኑ)። ተደጋጋሚ የሆነ አጽንዖት አለ፣ መዝሙር ላይ፣ በእስራኤል አምላክ ሁለንተናዊ ገጽታ (መዝ. 9:11ለ፤ 18:47፣49፤ 105:1፤ 145:12-13)። የአሀዳዊነት (አንድ አምላክ) አንድምታ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 2፡7 ላይ) አንድ ብቸኛ እውነተኛ አምላክ አለ፣ እሱም ሰዎችን ሁሉ በአምሳሉ የፈጠረ፣ ለኅብረት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ሁለንተናዊ የመዋጀት ዕቅድ፣ መዝ. 2 መግቢያ ላይ)።

**57፡10** ይህ ቁጥር የሚደግመው ሰውኛ ዘይቤ የተደረጉትን የእግዚአብሔር አገልጋዮች ነው (ማለትም፣ ሄሰድ እና ኢሜት) ከቁጥር 3። እነርሱ ሁለቱም ከሰማያትና ከደመናት "በላይ" እንደሆኑ ተብሎላቸዋል (ማለትም፣ የዚህ ፕላኔት ከባቢ አየር)፣ እሱም የሚጠቅሰው

1. ታላቅነታቸውን
2. ከእግዚአብሔር መገኘታቸውን

**57፡11** ይህ ቁጥር 5ን ይደግማል። እሱም የሚያገለግለው የእግዚአብሔርን ታላቅነት ለመግለጽ ነው (ማለትም፣ እሱ በፍጥረቱ ላይ ያለውን ሉዓላዊነት)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "በክንፎችህ ጥላ፣" የሚለውን ዘይቤ አብራራ ቁ. 1።
2. ሦስቱን የመለኮት ስሞች ዘርዝር፣ ቁ. 2 ላይ፣ አንድምታቸውንም አብራራ።
3. "ሰማይ"ን ግለጽ።
4. የእግዚአብሔር ባሕርይ ገጽታዎች ለምን ሰውኛ ሆኑ?
5. ቁጥር 9ን አብራራ፣ ከአሀዳዊነት አኳያ።

# መዝሙር 58
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጆት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ለኃጢአተኛ ቅጣት መጸለይ<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ፤ የዳዊት ቅኔ | በኃጢአተኛ ላይ ተገቢ ፍርድ | ርግማን በጠላቶች ላይ | ጸሎት ለእግዚአብሔር ኃጢአተኛን እንዲቀጣ | የምድር ፈራጆች ዳኛ |
| 58:1-5 | | | | |
| | 58:1-2 | 58:1-2 | 58:1-2 | 58:1-2 |
| | 58:3-5 | 58:3-5 | 58:3-5 | 58:3-5 |
| 58:6-9 | 58:6-8 | 58:6-9 | 58:6-9 | 58:6-8 |
| 58:10-11 | 58:9-11 | | | 58:9-11 |
| | | 58:10-11 | 58:10-11 | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የሚመለከተው ጻድቅ ያልሆኑ ፈራጆችንና የእነርሱን ፍትሐዊ ያልሆነ፣ የራስ ተኮር ሐሳብ ነው።

ለ. እነዚህ መሪዎች (ማለትም፣ ሙኩቶች) ከልደታቸው ኃጢአተኛ እንደሆኑ ተገልጸዋል (መዝ. 51፡5፣ ማለትም፣ የምስራቅ ግነታዊ ዘይቤ)።

ሐ. የእግዚአብሔር ፍርድ በእነዚህ ሃይማኖታዊ አስመሳዮች፣ በዓመጻ የተሞሉ ላይ ይወድቃል።

መ. ጻድቅ ይደሰታል፣ እግዚአብሔር በክፉና በተበላሸ ላይ በተቃርኖ ሲሠራ። እሱም በጽድቅ ይገዛል፣ አንድ ቀን በአዲስ ዓለም ላይ!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 58፡1-5**
**1በእውነት ጽድቅን ብትናገሩስ፥**
**የሰው ልጆች ሆይ፥ በቅን ትፈርዳላችሁ**
**2በልባችሁ በምድር ላይ ኃጢአትን ትሠራላችሁና፥**
**እጆቻችሁም ግፍን ይታታሉና።**
**3ኀጥአን ከማኅፀን ጀምረው ተለዩ**
**ከሆድም ጀምረው ሳቱ፥ ሐሰትንም ተናገሩ።**
**4ቍጣቸው እንደ እባብ መርዝ ነው፥**
**እንደ ምድር አውሬም ጆሮዋ የተደፈነ ነው፥**

[5]አዋቂ ሲደግምባት
የአስማተኛውን ቃል እንደማትሰማ።

**58፡1** *የመጀመሪያውን ስንኝ ለመተርጎም አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ። እሱም በግልጽ ተመሳሳይ ትይዩ ግንኙነት ይኖረዋል፣ ከሁለተኛው ስንኝ ጋር።*

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"እማልክት ሆይ"** |
| **አኪጀት** | **"ጸጥ ያላችሁ እናንተ"** |
| **አየተመት** | **"እናንተ አማልክት"** |
| **አኢመቅ** | **"መለኮት እንደሆናችሁ"** |
| **ጄፒኤስአኤ** | **"ኃያላን ሆይ"** |
| **የተእመቅ** | **"እናንተ ገዥዎች"** |

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 268) "በጸጥታ" ለሚለው ቃል "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ) እናም "በርግጥ የምትናገረው የጸጥታ ጽድቅ ነውን?" የመሰለ ትርጉም ይኖረዋል፣ ማለትም፣ አንተ በርግጥ የምትናገረው ጽድቅን በጸጥታ ለመሸሸግ ነውን?

ኤምቲ ወለא አለው፣ እሱም ከቢዲቢ 48 ጋር የሚዛመድ (ጸጥታ) ወይም ቢዲቢ 18 III (ኃያላን ጌቶች)። ምንም ይሁን ምን "የሰዎች ልጆች" ከሚለው ጋር ትይዩ መሆን ይኖርበታል፣ ስንኝ ሁለት ላይ። ስለዚህ "አማልክትን" ሊያመለክት አይችልም፣ ነገር ግን የሕዝብ መሪዎችን እንጂ (ማለትም፣ ፈራጆች፣ መዝሙር 82፤ ዘጸ. 22:8-9፤ ዘዳ. 1:17፤ 2 ዜና. 19:6) "ሙክት" ከሚለው ሥር (ቢዲቢ 17፣ ዘጸ. 15:15፤ 2 ነገ. 24:15፤ ሕዝ. 17:13፤ 31:11፤ 32:21፤ 34:17)።

LXX፣ ፔሺታ፣ እና ቫልጌት አናባቢዎቹን ይቀይራሉ ተቃርኖን ለማምጣት፣ "እናንተ በርግጥ ጽድቅን ትናገራላችሁን?"

**58፡2-5** እነዚህ ቁጥሮች የእነዚህን መሪዎች እውነተኛ ተፈጥሮ ይገልጣሉ።

1. በልባችሁ ኃጢአትን ትሠራላችሁ፣ ቁ. 2
2. እጆቻችሁ ግፍን ይታታሉና
3. ከማኅፀን ጀምረው ተለዩ (ሙሉ ማስታወሻውን ተመልከት፣ መዝ. 51፡5፤ ይህ ምስራቃዊ ግነታዊ ዘይቤ ምስያ ነው፣ ሥነ-መለኮታዊ ሳይሆን)
4. በሕይወታቸው ሁሉ ሐሰትን ይናገራሉ
5. የእባብ መርዝ አላቸው
6. የአስማተኛውን ቃል እንደማይሰማ ("ደጋሚ") — ቢዲቢ 538፣ ኬቢ 527፣ እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው ለእባብ አስማተኞች ነው። የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ሰዎች ያስቡ የነበሩት የዋሽንት ድምጽ (ወይም ድምጽ) እባብን ጸጥ ያሰኘዋል፣ ነገር ግን ዛሬ እኛ የምናውቀው የዋሽንት የራሱ ዜማዊ ንዝረት ነው፣ ድምጽ ሳይሆን።

   ሥነ-መለኮታዊው ነጥብ የሚሆነው እነርሱ ፈቅደው እግዚአብሔርን አለመስማታቸው ወይም እነርሱ ወደ መደምደሚያ መድረሳቸው ነው።

   እኔ "ድንቅ" ከአስማት ጋር እኩል እንደሆነ እዚህ አላስብም፣ ነገር ግን ባህላዊ እባብ ለሕዝብ መዝናኛ ይተውናል።

**58፡2 "በምድር"** በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን መሬት ነው፣ ምድርን ሳይሆን። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር መዝ. 1፡2። ዐውደ-ጽሑፍ ብቻ የቃልን ፍች ሊወስን እንደሚችል አስታውስ።

## መዝሙር ፡ 58፡6-9

**[6]እግዚአብሔር ጥርሳቸውን በአፋቸው ውስጥ ይሰብራል**
**እግዚአብሔር የአንበሶቹን መንጋጋቸውን ያደቅቃል።**
**[7]እንደሚፈስስ ውኃ ይቀልጣሉ**
**እስኪያደክማቸው ድረስ ፍላጾቹን ይገትራል።**
**[8]እንደሚቀልጥ ሰም ያልቃሉ እሳት ወደቀች፥**
**ፀሐይንም አላዩአትም።**
**[9]እሾኻችሁ ሳይታወቅ በትር ሆነ**
**ሕያዋን ሳላችሁ በመዓቱ ይነጥቃችኋል።**

**58፡6-9** ይህ አንጓ ለእግዚአብሔር የሚደረግ ጸሎት ነው (ሁለቱም ኤሎሂም እና ያህዌ ጥቅም ላይ የዋሉበት) በእነዚህ ፈራጆች ላይ ፍርድ እንዲደረግ፣ በምስላዊ፣ ገላጭ ሐረጋት።

1. ጥርሳቸውን ይሰብራል – ቢዲቢ 248፣ ኬቢ 256፣ *ቃል ተተኳሪ* ("ጥርስ" እና "መንጋጋ"፤ ትይዩ ነው፣ ኢዩኤል 1:6 ላይ)
2. *ያደቅቃል* "ይሰባብራል") *መንጋጋዎች* (ቢዲቢ 1069) የደቦል አንበሶችን – ቢዲቢ 683፣ ኬቢ 736፣ *ቃል ተተኳሪ* (ቁ. 1 እና ቁ. 2 ትይዩ ናቸው፣ ፍርድ ኃጢአት ባደረጉበት በዚያው ስፍራ ላይ ይከሰታል [ማለትም፣ በቃላቸው/በአስተያየታቸው])
3. እንደሚፈስስ ውኃ ይፈስሳሉ – ቢዲቢ 549፣ ኬቢ 541፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
4. ቀስታቸው የማይረባ ሆነ (የዕብራይስጥ ፈሊጥ፣ ርግጠኝነት የሌለው፣ ነገር ግን የሚያመለክተው የእነርሱን ልክ ያይደለ ሐሳብና ክስ ነው)
5. እንደ ሰም ይሁኑ (ቢዲቢ 117፣ በብኪ እዚህጋ ብቻ ያለ) እሱም ቀልጦ የሚጠፋ (ቢዲቢ 588፣ ይህ ዓይነት እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪጋ፣ "መሚሚት" ቢዲቢ 587 ነው) ተያይዞ እንደሚሄደው — ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፤ ታሳቢው "የመሆን" ግሥ በተጽዕኗዊ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው
6. እንደ ሴት ጭንገፋ ይሁንባቸው፣ ፀሐይን እንደማያይ – ቢዲቢ 302፣ ኬቢ 301፣ *ቃል* የተጠናቀቀ (ምንም እንኳ ያልተጠናቀቀ ባይሆንም የወዲያው ጽንሰ-ሐሳብ ይሻዋል፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ እንዲውል)

ቁጥር 8 ላይ ምን እንደተባለ በርግጠኝነት ለመረዳት ያለው ችግር፣ በ"ሰም" እና "ጭንገፋ" መካከል ያለው ትይዩነት ስሕተት ያለው መሆኑ ነው፣ እንዴት እንደሆነ ግን ርግጠኝነት የለውም። በሁለተኛው ስንኝ ላይ ያለው ቃል ከ "ሰም" እና "ከመቅለጥ" ባለፈ ርግጠኝነት ያለው ነው። ኒዶቲ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 30 የሚለው "ሰም" እንደ "ጭንገፋ" መረዳት እንዳገኘ ነው።

7. ይህ በዕብራይስጥ አስቸጋሪ ቃል ነው (ኤቢ እንዲያውም ሊተረጉመው አይሞክርም)። በርካታ ሐሳቦች ተሰንዝረዋል። መሠረታዊው ነጥብ የሚሆነው ለማብሰያው ማሰሮ የሚያስፈልገው ሙቀት ጠፍቷል፣ መብሉን ከማሞቁ በፊት የሚል ነው (ማለትም፣ ፈጣን የእሳት መለኮሻ እንኳ)።

ልክ እንደ ቀዳሚዎቹ የቅኔ ስንኞች፣ እነዚህ ያልተጠናቀቁ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ ይመስላሉ፣ ቁጥር 6 ላይ ካሉት የጸሎት ጥያቄ ተተኳሪዎች ጋር ለማያያዝ።

**መዝሙር ፡ 58፡10-11**

**[10]ጻድቅ በቀልን ባየ ጊዜ ደስ ይለዋል**
**በኃጢአተኛው ደምም እጁን ይታጠባል።**
**[11]ሰውም። በእውነት ለጻድቅ ፍሬ አለው**
**በእውነት በምድር ላይ የሚፈርድ አምላክ አለ ይላል።**

**58፡10-11** እሱ ዘመናዊ ተርጓሚዎችን ዘወትር እንዳሳሰባቸው ነው፣ መዝሙራት ይህን የመሰሉ አስፈሪ ፍርዶችን በጸሐፊው ጠላቶች ላይ እንዲሆኑ በመጠየቃቸው። ይህንን ለመመልከት አንደኛው መንገድ እነዚህ ጠላቶች እግዚአብሔርን እያጠቁ ነው፣ የእርሱን ሕዝብ ያላግባብ በሚያጠቁበት ጊዜ። ስለዚህ ቀደም ብሎ የተቀመጠው ፍርድ (ማለትም፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30) በእነርሱ ላይ በቀጥታ ይወድቅባቸዋል። ስለዚህ፣ እሱ የበቀል ወይም የብቀላ ጥሪ አይደለም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ፍትሕና ፍጻሜ እንጂ፣ ስለዚህ ሁሉም ይመለከታሉ፣ ጻድቁ እግዚአብሔር በእስራኤል እንዳለ (ዘዳ. 32:34-43፤ መዝ. 79:10፤ 94:1-11፤ 149:7-9)።

ቁጥር 10ለ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ግነታዊ ዘይቤ ነው፣ ለወታደራዊ ድል (መዝ. 68:23)።

**58፡11** ከአእት መጽሐፍ ቅዱስ ጋር እስማማለሁ፣ ማለትም ቃል የድርጊት አንቀጽ፣ ተባዕታይ፣ የብዙ ቁጥር፣ የግርማው የብዙ ነው፣ እሱም የያህዌን የጽድቅ ፍርድ የሚያመለክት።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት _መመሪያ_ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ማንን ነው የሚመለከተው?
2. ቁጥር 3 የዋነኛ ኃጢአትን ዶክትሪን ያስተምራልን?
3. ቁጥር 4ለ የሚያስተላልፈው ምን ዓይነት መንፈሳዊ እውነት ነው?
4. ቁጥር 8 ላይ ያለውን የተመሳሳይ ትይዩነት እጥረት አብራራ።
5. ቁጥር 10-11 የበቀል መንፈስን ያስተምራሉን? ለምን ወይም ለምን ሳይሆን?

# መዝሙር 59
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጸሎት ከጠላቶች ለመታደግ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ፤ ሳኦል ይገድሉት ዘንድ ቤቱን እንዲጠብቁ በላከ ጊዜ የዳዊት ቅኔ። | የተረጋገጠ የኃጢአተኛ ፍርድ | ጸሎት ከጠላቶች ለመታደግ | የደኅንነት ጸሎት | በኃጢአተኛ ላይ |
| 59:1-8 | 59:1-2 | 59:1-2 | 59:1-2 | 59:1-2 |
| | 59:3-4 | 59:3-4 | 59:3-4 | 59:3-4ለ |
| | | | | 59:4ሐ-5 |
| | 59:5 | 59:5 | 59:5 | |
| | 59:6-7 | 59:6-7 | 59:6-7 | 59:6 |
| | | | | 59:7 |
| | 59:8-9 | 59:8-10 | 59:8-10 | 59:8-9ሀ |
| 59:9-15 | | | | 59:9ለ-10 |
| | 59:10 | | | |
| | 59:11-13 | 59:11-13 | 59:11-15 | 59:11 |
| | | | | 59:12 |
| | | | | 59:13 |
| | 59:14-15 | 59:14-15 | 59:14-15 | 59:14 |
| | | | | 59:15 |
| 59:16-17 | 59:16-17 | 59:16-17 | 59:16-17 | 59:16 |
| | | | | 59:17 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. እንደገናም “ጠላቶች” እነማን ናቸው የሚለው ጥያቄ ይከሰታል። በዚህ መዝሙር ላይ የሚያመለከተው የአሕዛብን ወራሪዎች ይመስላል (ዝኪ. ቁ. 5፣6፣7፣8፣11፣13፣14፣15)። ቁጥር 8 አንደኛውን መዝሙር 2፡4ን ያስታውሳል።

ለ. መዝሙረኛው በግልጽ ያስቀምጣል፣ መጠቃቱን፣ ነገር ግን የሆነ ነገር በማድረጉ ምክንያት አይደለም (ዝኪ. ቁ. 3ሐ፣ 4ሀ)። ጥቃቱ የመጣው እሱ/እነርሱ የያህዌ ሰዎች በመሆናቸው ይመስላል።

ሐ. የኪዳኑ መለኮት መጠሪያዎች ተገንዘብ።
1. አምላኬ ሆይ፣ ቁ. 1 – ኤሎሂም ይሆናል፣ እንደ ቁጥር 8 ከመጨረሻው ፊደል ጋር፣ በቀጣዩ ቃል

2. ያህዌህ ሆይ፣ ቁ. 3፣5፣8 – ቢዲቢ 217
3. የሠራዊት አምላክ (*ኤሎሂም ጸባዖት*)፣ ቁ. 5 – ቢዲቢ 43 and 838፤ *ወታደራዊ ፍችዎች*
4. የእስራኤል አምላክ፣ ቁ. 5 – ቢዲቢ 43 አወቃቀር ቢዲቢ 975
5. ጉልበቴ ሆይ – ቢዲቢ 738
6. እግዚአብሔር መጠጊያዬ/ምሽጌ ነው፣ ቁ. 9 – ቢዲቢ 43 እና ቢዲቢ 960 l
7. እግዚአብሔር ለእኔ ቸር ነው፣ ቁ. 10፣17 – ቢዲቢ 43 እና ቢዲቢ 338
8. ጌታችን፣ ጋሻችን ነው ወይም አዶን ጋሻችን ነው፣ ቁ. 11 – ቢዲቢ 10 እና ቢዲቢ 171
9. እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ ቁ. 13 – ቢዲቢ 43 (*ኤሎሂም*)
10. ጉልበቴ ሆይ፣ ቁ. 16 – ቢዲቢ 738
11. እግዚአብሔር ምሽጌ ሆይ፣ ቁ. 17 – እንደ ቁ. 5

## የቃልና የሐረግ ጥናት

***መዝሙር ፡ 59፡1-8***

**[1]አምላኬ ሆይ፥ ከጠላቶቼ አድነኝ**
**በላዬም ከቆሙት አስጥለኝ።**
**[2]ከግፍ አድራጊዎች ታደገኝ፥**
**ከደም ሰዎችም አድነኝ።**
**[3]እነሆ፥ ነፍሴን ሸምቀውባታልና፥**
**ብርቱዎችም በላዬ ተሰበሰቡ።**
**አቤቱ፥ በበደሌም አይደለም፥ በኃጢአቴም አይደለም።**
**[4]ያለ በደል ሮጥሁ ተዘጋጀሁም**
**ተነሥ፥ ተቀበለኝ፥ እይም።**
**[5]አንተም አቤቱ፥ የኃያላን አምላክ፥ የእስራኤል አምላክ፥**
**አሕዛብን ሁሉ ትጐበኛቸው ዘንድ ተነሥ**
**ዓመፅ የሚያደርጉትን ሁሉ አትማራቸው። ሴላህ**
**[6]ማታ ይመለሱ እንደ ውሾችም ይራቡ፥**
**በከተማም ይዞሩ።**
**[7]እነሆ፥ በአፋቸው አሰምተው ይናገራሉ**
**ሰይፍም በከንፈሮቻቸው አለ**
**ማን ይሰማል? ይላሉ።**
**[8]አንተ ግን አቤቱ፥ ትሥቅባቸዋለህ፥**
**አሕዛብንም ሁሉ ትንቃቸዋለህ።**

**59፡1-2** *መዝሙሩ በሦስት ተተኳሪዎች እንደሚጀምር ተገንዘብ (የጸሎት ጥያቄዎች ከጠላቶች ለመታደግ)።*
1. አድን፣ ቁ. 1 – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
2. አድን፣ ቁ. 2 – እንደ ቁ. 1
3. አድን – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 28:9፤ 31:16፤ 71:2፤ 86:2፣16

ሁለቱም ጥቅም ላይ ውለዋል መዝ. 7:1፤ 22:20-21፤ 31:2-3፣15-16፤ 33:16-17፤ 34:17-18፣ ወዘተ ላይ። እሱም ተደጋጋሚ ጸሎት ነው ለዕርዳታ!

የጠላቶች ባሕርይ እንዴት እንደሆነ ተገንዘብ።
1. በእኔ ላይ የተነሡት
2. ክፋትን የሚሠሩ
3. ደም አፍሳሽ ሰዎች

ጠላቶች በዚህ መዝሙር ላይ የሚመስሉት የውጭ ወራሪዎች ናቸው።
1. አሕዛብን ሁሉ ቅጣ፣ ቁ. 5
2. በከተማ ይዞሩ (ማለትም፣ ይከበቡ)፣ ቁ. 6
3. ያገሳሉ... ሰይፍ፣ ቁ. 7
4. ያህዌ አሕዛብን ሁሉ ይንቃቸዋል፣ ቁ. 8
5. ሕግህን እንዳይረሱ አትግደላቸው፣ ቁ. 11
6. የያዕቆብ አምላክ እስከምድር ዳርቻ ይገዛል፣ ቁ. 13
7. በከተማም ይዞሩ፣ ቁ. 14 (ቁ. 2ን ተመልከት)
8. ቁ. 15 የከበባ ምስያ ነው

**59፡3-4*ሀ*** በእነዚህ ቁጥሮች የነጠላ ቁጥሩ "እኔ" የእስራኤልን መሪ ያመለክታል። በእርሱ ላይ የሚደረግ ጥቃት በኪዳን ሕዝቡ ላይ የሚደረግ ጥቃት ነው። አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ የውጭ ወራሪዎች የውስጥ ርዳታ ይኖራቸው እንደሁ።

ደራሲው የራሱን ጽድቅ በማስረገጥ ማጽናቱን ተገንዘብ ያለ ምክንያት የተጠቃ መሆኑን (ዝከ. ቁ. 3ሐ፣ 4ለ)። ጠላቶቹ ያጠቁት ከእስራኤል አምላክ ጋር በመዛመዱ ነው (መዝሙር 2)።

**59፡4ለ-5** እነዚህ ሁለት ቁጥሮች በሦስት ተተኳሪዎች ተያይዘዋል፣ መለኮት የማዳን ሥራ እንዲሠራ በመጠየቅ።

1. ተነሥ፣ ቁ. 3ለ – ቢዲቢ 734፣ ኬቢ 802፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 7:6፤ 35:23፤ 44:23፤ 57:8 (ሦስቴ)፤ 73:20፤ 80:2፤ 108:2
2. ተመልከት፣ ቁ. 46 – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ1157፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 9:13፤ 25:18፣19፤ 80:14፤ 84:9፤ 119:153፣159፤ 139:24
3. ንቃ፣ ቁ. 5 – ቢዲቢ 884፣ ኬቢ 1098፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ መዝ. 35:23፤ 44:23

◘ ***"ዕርዳኝ"*** ይህ በጥሬው "አግኘኝ" ነው። ይህ ግላዊ ገጽታ ቁጥር 10ሀ ላይ ተደግሟል።

◘ ***"የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሆይ"*** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች መዝ. 1፡1 ላይ።

◘ ***"አትማራቸው"*** ይህ አሉታዊ ግሥ (ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው) እሱም በመዝሙር ዘወትር ላይ ጥቅም ይውላል (መዝ. 4:1፤ 6:2፤ 9:13፤ 25:16፤ 26:11፤ 27:7፤ 30:10፤ 41:4፣10፤ 51:1፤ 56:1፤ 57:1፣ ወዘተ.)። እዚህጋ መዝሙረኛው እግዚአብሔርን የሚጠይቃው ለጠላቶቹ ምሕረትን እንዳያሳይ ነው፣ ምክንያቱም እነርሱ ተንኮለኛና በደለኛ በመሆናቸው (መዝ. 109:14፤ ኢሳ. 2:9፤ ኤር. 18:23)።

**59፡6-7** በርካታ ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች አሉ፣ ቁጥር 6-7 እንደ አንጓ ያላቸው፣ እንዲሁም አዲስ አንጓ ቁጥር 8-10 ላይ የሚጀምሩ። ይሄንንም መዝሙር እንደ ሎጂካዊ ምድቡ ለመከፋፈል አዳጋች ነው።

ቁጥር 6-7 ጠላቶቹን የሚገልጻቸው እንደ
1. አልቃሻ ውሾች
2. ተልከስካሽ ውሾች
   ሀ. የከበባ ዘይቤ (ዝከ. 59፡14-15)
   ለ. በምግብ ፍለጋ መጠመዳቸውን የሚያሳይ ዘይቤ (59፡15)
3. ማግሳት... ሰይፎች፣ ቁ. 7
4. እግዚአብሔርን አለመፍራት (ማለትም፣ "ማን ይሰማል?" ይላሉ፣ ኢዮብ 22:13፤ መዝ. 10:4፣11፣13፤ 64:5፤ 73:11፤ 94:7፤ ኢሳ. 29:15፤ ሕዝ. 8:12)። እነርሱ አንድም
   ሀ. እስራኤላውያን ተግባራዊ አምላክ-የለሾች
   ለ. ባዕድ አምልኮተኞች/ጣዖት አምላኪዎች

**59፡8** ቁጥር 8 እኔን የሚያስታውሰኝ
1. መዝሙር 2፡4
2. መዝሙር 37፡13

ይህ ቁጥር ለማስረዳት የሚሞክረው ጠላቶች አሕዛብ፣ ጣዖት አምላኪ ወራሪዎች መሆናቸውን ነው (ዝከ. ቁ. 5፣6፣7፣8፣11፣13፣14፣15)።

ቁ. 8 ላይ ያሉት ግሦች ሁለቱም ቃል ተተኳሪዎች ናቸው፣ ቀጣይነት ያለውን ድርጊት የሚገልጹ (ማለትም፣ ያህዌ ይስቅባቸዋል... ይንቃቸዋልም፣ አሕዛብ ላይ። ባለማመናቸውና በእርሱ ሕዝብ ላይ በሚያሳዩት ትዕቢት እና ጥቃት)።

**መዝሙር ፡ 59፡9-15**

**[9]እግዚአብሔር መጠጊያዬ ነውና**
**ኃይሌን ወደ አንተ አስጠጋለሁ።**
**[10]የአምላኬ ቸርነቱ ይገናኘኛል**
**አምላኬ በጠላቶቼ ላይ ያሳየኛል።**
**[11]ሕግህን እንዳይረሱ አትግደላቸው**
**አቤቱ ጋሻዬ፥**
**በኃይልህ በትናቸው አውርዳቸውም።**
**[12]ስለ አፋቸው ኃጢአት ስለ ከንፈራቸውም ቃል፥**
**መርገምንና ሐሰትን ስለሚናገሩ፥**
**በትዕቢታቸው ይጠመዱ።**
**[13]በቍጣ አጥፋቸው፥ እንዳይኖሩም አጥፋቸው**
**የያዕቆብም አምላክ**
**እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ እንዲገዛ ይወቁ።**
**[14]ማታ ይመለሱ እንደ ውሾችም ይራቡ፥**
**በከተማም ይዞሩ።**
**[15]እነርሱም መብል ለመፈለግ ይበተኑ**
**ያልጠገቡ እንደ ሆነም ያንጐረጕራሉ።**

**59፡9-13** በርካታ የመለኮት መጠሪያዎች አሉ። ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ሐ።

**59፡9**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | ***"ኃይሉ"*** |
| **አኪጀት** | ***"ኃይሉ"*** |
| **አየተመት፤ አኢመቅ፤** | |
| **ጀፒኤስአኤ** | ***"ኃይሌ"*** |

**አእቅ** **"ኃይልህ"**

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 271) ለ "ኃይሌ" "መ" ደረጃ ይሰጣል፣ (እጅግ አጠራጣሪ)። ይህ ምናልባት የተመሠረተው በተመሳሳይ ቃላት ይሆናል፣ ቁጥር 18 ላይ። እሱም የመለኮት መጠሪያ ነው።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | ***"ከኃይሉ የተነሣ"*** |
| **አኪጀት** | **"አንተ ኃይሉ ሆይ"** |
| **አየተመት፣ ጀፒኤስአኤ** | **"ኃይሌ ሆይ"** |
| **አኢመቅ፣ የተእመቅ** | **"ኃይሌ"** |
| **LXX** | **"ብርታቴ ሆይ"** |

ይህ ሌላው የመለኮት መጠሪያ እንደሆነ አስባለሁ (መዝ. 21:1፤ 28:7፣8፤ 59:17፤ 81:1፤ 118:14)። እሱም "እግዚአብሔር መሸሸጊያዬ" ከሚለው ጋር ትይዩ ነው።

▣ **"አንተን እጠብቃለሁ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581) ቃል ተጓዳኝ ነው፣ መዝ. 130፡6። መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ለማየት ናፍቋል፣ ከእርሱም ጋር እንዲሆን!

**59፡10** ይህ ሌለኛው የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው (ማለትም፣ "እግዚአብሔር ለእኔ ቸር ነው")፣ አኪጀት "የኔ መሐሪ አምላክ" የሚል አለው፣ እንዲሁም ጀፒኤስአኤ "የእኔ ታማኝ አምላክ።"

▣ **"በጠላቶቼ ላይ አያለሁ"** ይህም ሌላው ባህላዊ ፈሊጥ ነው፣ ለድል (መዝ. 23:5፤ 54:7፤ 91:8፤ 92:11፤ 112:8፤ 118:7)።

**59፡11** ይህ ቁጥር ያስገርመኛል። እሱም የሚያስታውሰኝ፣ ያህዌ ከዕብራውያን ነገዶች ጋር እንዴት እንደሚኖር ነው፣ በኢያሱ አማካኝነት የተመሸጉት ከተሞች ድል ከተነሡ በኋላ። እያንዳንዱ ነገድ የየራሱን ግዛት በወታደራዊ አቋም ድል ማድረግ ይጠበቅበታል፣ ከከነአናውያን ነገዶች። እግዚአብሔር ለእነርሱ አላደረገላቸውም። እነርሱ በእምነት መንቀሳቀስ ነበረባቸው። ጥቂት ተቃዋሚዎችን ትቶባቸዋል፣ በእምነት እንዲያድጉ፣ በእርሱ፣ እና በራሳቸውም።

የግሥ መልኮች

1. አትግደላቸው፣ ቁ. 11 – ቢዲቢ 246፣ ኬቢ 255፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
2. በትናቸው ቁ. 11 – ቢዲቢ 631፣ ኬቢ 681፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
3. አውርዳቸው ቁ. 11 – ቢዲቢ 432፣ ኬቢ 434፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

4-5 አጥፋቸው ቁ. 13 – ቢዲቢ 477፣ ኬቢ 476፣ *ፔል ተተኳሪ* (ሁለቴ)

6.ከዛን በኋላ እንዳይኖሩ – ቢዲቢ 34 II (ግሥ የለውም)

እነዚህ ትእዛዛት በቁ.11ሀ ተሻሽለዋል። መደነጋገር ያለ ይመስላል በ"አይደለም"( ነአ) – ቢዲቢ 39) እና "ኤል" (ነአ ፣ ለመለኮት አጠቃላይ ስም በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) – ቢዲቢ 42 II)። ይህ የኤቢ አስተያየት ነው (ገጽ 71)።

▣ **"ሕዝቤ እንዳይረሱ"** ግሥ (ቢዲቢ 1013፣ ኬቢ 1489፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) ደግሞም ዘዳ. 8:11-20 ላይ ይከሰታል፣ እዚያም ያህዌ ሕዝቡን ያስጠነቅቃል፣ ብልጽግናቸውም ሆነ ድላቸው በእነርሱ እንደሆነ እንዳያስቡ!

▣ **"ጋሻችን"** ይህ ምስያ ወደ ኋላ ተመልሶ ይሄዳል፣ ያህዌ በመነሻው ከአብርሃም ጋር የተነጋገረበት እና ከእርሱ ጋርና ከዘሩ ቃል ኪዳን የገባበት (ዘፍ. 15:1፤ ዘዳ. 33:29)። እሱም መዝሙር ላይ ተደጋጋሚ ነው (መዝ. 3:3፤ 5:12፤ 28:7፤ 115:9-11)። እሱም አምላክን እንደ መከታ ይገልጻል!

**59:12 "በትዕቢታቸው ይጠመዱ"** – ቢዲቢ 539፣ ኬቢ 530፣ *ኒፋል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*። የሰዎች ኩራትና ትዕቢተኝነት

1. የውድቀት ውጤት ነው
2. በያህዌ ፊት አስጸያፊ ነው

እሱ አይታገሠውም (ኢሳ. 2:11-12፤ 5:15፤ 10:33፤ ሰፋ. 3:11)። ለሰዎች ትምክህት እንደ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምሳሌ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መመካት መዝ. 20:7 ላይ።

**59:13 "የያዕቆብ አምላክ እንዲገዛ ይወቁ**
**እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ"** ይህ ሁለንተናዊ ነገር ዋነኛ ነው፣ አምላክ በምድራችን ምን እያደረገ እንደሆነ ለመረዳት (መዝ. 2:8፤ 58:11፤ 67:7፤ 72:8፣17፤ 96:13፤ 98:9፤ ኢሳ. 45:22፤ 49:6፤ 52:10፤ ኤር. 16:19፤ ሚኪ. 5:4፤ ማቴ. 25:32)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ፣ የመዝሙር 2 መግቢያ ላይ።

▣ **"ሴላህ"** መዝ. 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻና የመዝሙር መግቢያ VII ተመልከት።

**59:14**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አየተመት፣ ጀፒኤስአኤ** | **"ያልቅሱ"** |
| **አኪጀት** | **"ያላዝኑ"** |

ይህ ሥር (ቢዲቢ 534 II) ፍችው የሚሆነው

1. ሌሊቱን ማሳለፍ – ቢዲቢ 533 I (ይህ የኤምቲ አመላካች ነው፣ መዝ. 55:7)

2. ማንጎራጎር – ቢዲቢ 534 ll

**መዝሙር ፡ 59፡16-17**

[16]**እኔ ግን ለኃይልህ እቀኛለሁ**
**በምሕረትህም ማልዶ ደስ ይለኛል**
**በመከራዬ ቀን መጠጊያዬና**
**አምባዬ ሆነኸኛልና።**
[17]**ረዳቴ ሆይ፥ ለአንተ ለአምላኬ እዘምራለሁ**
**አንተ፥ አምላኬ፥ መጠጊያዬ ምሕረቴም ነህና።**

**59፡16-17** መዝሙረኛው ያነጻጽራል (ማለትም፣ "ለእኔ ግን") የእርሱን የሕይወት ስልት እና ሐሳብ ከእነርሱ ጋር።

1. እኔ ግን በኃይልህ እቀኛለሁ፣ ቁ. 16
2. ለምሕረትህም በደስታ እዘምራለሁ፣ ቁ. 16
3. ምስጋናም እዘምርልሃለሁ፣ ቁ. 17

ለእነዚህ ያህዌን ለሚያወድሱ መዝሙሮች ምክንያት

1. መጠጊያው በመሆኑ (ቢዲቢ 960 l)
2. የእርሱ መሸሸጊያ በመሆኑ (ቢዲቢ 631) በመከራው ጊዜ፣ ኤር. 16፡19
3. ዐምባው በመሆኑ (ቢዲቢ 960 l)፣ መዝ. 9፡9፤ 59፡9፤ 62፡2፣6
4. ቸርነቱን ስላሳየው (ቢዲቢ 338)

በርካታ ቁልፍ ሥነ-መለኮታዊ ቃላት፣ ያህዌን የሚገልጹት በዚህ ሐረግ ላይ ተደግመዋል።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ጠላቶች እነማናቸው? ሁለት ወገኖች እንዳሉ የሚመስለው ለምንድነው?
2. መዝሙረኛው ኃጢአት-የለሽ እንደሆነ እየገለጸ ነውን፣ ቁጥር 3ሐ፣ 4ሀ ላይ?
3. "ተነሥ" እና "ንቃ" ከሚሉት ጀርባ ያለው ምስያ ምንድነው?
4. በዚህ መዝሙር ላይ ሁለንተናዊ ነገሮችን ዘርዝር። አንድምታቸውስ ምንድነው?
5. ቁጥር 11 የሚያደነጋግር ይመስላል። ለምን?

## መዝሙር 60
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| በውጊያ ላይ ድል በመሆን ማዘንና ለዕርዳታ መጸለይ<br>ኤምቲ መግቢያ ለመዘምራን አለቃ፤ የሶርያን ሁለቱን ወንዞችና የሶርያን ሶባልን ባቃጠለ ጊዜ ኢዮአብም ተመልሶ ከኤዶማውያን ሰዎች በጨው ሸለቆ አሥራ ሁለት ሺህ በገደለ ጊዜ ለትምህርት የዳዊት ቅኔ።<br>60:1-5 | አስቸኳይ ጸሎት የአምላክ ሞገስ እንዲመለስ | ከብሔራዊ ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት | የመታደግ ጸሎት | ከሽንፈት በኋላ ብሔራዊ ጸሎት |
| | 60:1-3 | 60:1-3 | 60:1-5 | 60:1-2 |
| | | | | 60:3-4 |
| | 60:4-5 | 60:4-5 | | |
| 60:6-8 | | | | |
| | | | | 60:5 |
| | 60:6-8 | 60:6-8 | 60:6-8 | 60:6 |
| | | | | 60:7 |
| 60:9-12 | | | | |
| | | | | 60:8 |
| | 60:9-12 | 60:9-12 | 60:9-12 | 60:9-10 |
| | | | | 60:11-12 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 60፡1-5**

**1 አቤቱ፥ ጣልኸን አፈረስኸንም**
**ተቈጣኸን ይቅርም አልኸን።**
**2 ምድርን አናወጥሃት አወክሃትም**
**ተናውጣለችና ቍስልዋን ፈውስ።**
**3 ለሕዝብህ ጭንቅን አሳየሃቸው፥**
**አስደንጋጩንም ወይን አጠጣኸን።**
**4 ከቀስት ፊት ያመልጡ ዘንድ፥**
**ለሚፈሩህ ምልክትን ሰጠሃቸው። ሴላህ**
**5 ወዳጆችህ እንዲድኑ**
**በቀኝህ አድን፥ አድምጠኝም።**

**60፡1-3** ይህ አንጓ የሚገልጸው መዝሙረኛው እንዴት እንደሚያስብ ነው፣ የእርሱ/እስራኤል ግንኙነት ከያህዌ ጋር ምን እንደሚመስል።
1. እሱ ትቶናል – ቢዲቢ 276፣ ኬቢ 276፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 44:9፤23፤ 74:1፤ 77:7፤ 108:11
2. እሱ ሰብሮናል – ቢዲቢ 829፣ ኬቢ 971፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ከመከላከያው ግንብ መፍረስ ጋር የሚያያዝ ይሆናል
3. ተቆጥቶናል – ቢዲቢ 60፣ ኬቢ 72፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
4. ምድራቸውን አናወጠ – ቢዲቢ 950፣ ኬቢ 1271፣ *ሂፊል*የተጠናቀቀ
5. ምድርን አወካት – ቢዲቢ 822፣ ኬቢ 954፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ያልፎ አልፎ ቃል፣ እዚህጋ ብቻ እና ከኤር. 22:14 ጋር በተያያዘ መልክ ያለው፣ እዚያም "መቁረጥ" በሚል የተተረጎመ
6. ሕዝቡ መከራን እንዲያዩ አደረገ – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ *ሂፊል*የተጠናቀቀ
7. ወይን እንዲጠጡ ሰጣቸው (ማለትም፣ ስካርና መንገዳገድ እንዲሆንባቸው) – ቢዲቢ 1052፣ ኬቢ 1639፣ *ሂፊል*የተጠናቀቀ፣ ጽዋው ለአሕዛብ ሊሆን ይችላል (ኤር. 25:16-26)፣ እናም አሁን ለኪዳኑ ሕዝብ ተሰጥቷል፣ በተመሳሳይ ውጤት (ኢሳ. 51:17፤22)

ሁሉም ግሦች የተጠናቀቁ እንደሆኑ ተገንዘቡ፣ እነርሱም የተመቻቸ ሁኔታን የሚገልጹ። ከዚህ አኳያ መዝሙረኛው ይጸልያል፣ እግዚአብሔር እንዲያደርግለት
1. መልሰን – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ *ፖለል* ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 80:3፤7፤19፤ 85:4፤ 126:1፤ ሰቆ. 5:21
2. ፈውስ (ማለትም፣ "መልስ፣" ኒዶቴ፣ ቅጽ. 3፣ ገጽ 1163) ምድርን – ቢዲቢ 950፣ ኬቢ 1272፣ *ቃል* ተተኳሪ፣ 2 ዜና. 7:14፤ ይህ ሊያመለክት የሚችለው የግንብን መፍረስ ነው፣ የቁ. 1ለ

ደግሞም የሚያሳየው እነዚህ ሁሉ የጸሎት ጥያቄዎች፣ ለእግዚአብሔር ዕርዳታ፣ ጥበቃ፣ ማዳን የተመሠረቱት በእርሱ ሕዝብ እምነትና የሕይወት ስልት ነው (2 ዜና. 6:37-39)። ሁሉም የእግዚአብሔር ተስፋዎች (ከመሢሑና ከእርሱ አገልግሎት ጋር ከተያያዙት በስተቀር ) ሁኔታዊ ናቸው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 25:10)።

## ልዩ ርዕስ፡ የያህዌ የኪዳን መስፈርት ለእስራኤል

የያህዌ መስፈርቶች (ቢዲቢ 981፣ ኬቢ 1371፣ *ቃል* የድርጊት አንቀጽ) በግልጽ ተቀምጠዋል፣ ተለጣጣቂ በሆኑ *ቃል* ያልተወሰነ አወቃቀሮች:
1. "እግዚአብሔርን እንዲፈሩ" – ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ ዘዳ. 4:29፤ 10:20
2. "በመንገዶቹ ሁሉ እንዲሄዱ" – ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ ዘዳ. 4:29
3. "እሱን እንዲወዱ" – ቢዲቢ 12፣ ኬቢ 17፣ cf. ዘዳ. 6:5፤ 10:15፤ ሙሉውን ማስታወሻ ተመልከት 5:10 ላይ
4. "ጌታ አምላክህን በሙሉ ልብህ እና በሙሉ ነፍስህ እንድታገለግል" – ቢዲቢ 712፣ ኬቢ 773፣ ዘዳ. 4:29፤ 6:5፤ 10:12፤ 11:13፤ 13:3፤ 26:16፤ 30:2፤6፤10
5. "የጌታን ትእዛዛት እና ሕግጋቱን እንዲጠብቁ" – ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581

ይህ ምንባብ ከሚኪያስ 6፡6-8 ጋር ተመሳሳይ ነው። ሁለቱም የሚናገሩት በየዕለት ሕይወት ላይ ተጽዕኖ ስለሚያሳድረው እምነት ነው!

**60፡1** እግዚአብሔር ሲተው (ዝኪ. ቁ. 1፣ 10) ሕዝቡን (ዝኪ. ቁ. 3፡5) አስደንጋጭ ነው! እግዚአብሔር ለእስራኤል ዓላማ እንዳለው ማስታወስ ይኖርብናል። እሷም ለመላው ዓለም የእግዚአብሔር ባሕርይና ዓላማ መገለጥ መንገድ እንድትሆን ነበር (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ፣ ሕዝ. 36፡22-38)። ይህም የታመነ የኪዳን ታዛዥነትን ይጠይቃል (1 ዜና. 28፡9)። በዘፍጥረት 3 ውድቀት ምክንያት አልቻሉም፤ ፍርድ ብቸኛው አማራጭ ነበር (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27፡30)።

"በቅድስናው" የሚለው ሐረግ ቁጥር 6 ላይ ለእግዚአብሔር ባሕርይ ብርቱ አስታዋሽ ነው፣ የእርሱ ሕዝብ ለአሕዛብ ብቃት ያለውና ሞዴል እንዲሆን ስለ መፈለጉ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት መዝ. 9፡10ለ ላይ)።

አዲስ አገባብ አስፈላጊ ነው። ይህም አዲስ አገባብ "አዲስ ኪዳን" ተብሎ ይጠራል (ኤር. 31፡31-34)። እሱንም አኪ. የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል በሚል የሚያብራራው።

**60፡4-5** ለእኔ ይህ የተለየ አንጓ ነው (አኪጀት፣ አየተመት)። ርዕሰ-ጉዳዩ ከቁጥር 1-3 ይለያል። ይህ አንጓ የሚያሳየው የያህዌን ድርጊት ነው፣ ከእስራኤል አኳያ።
1. ለሚፈሩት ምልክት ይሰጣቸዋል (ቢዲቢ 651፣ ማለትም፣ የሚታይ ምልክት ወይም መንገድ ለመገናኘት፣ ዘጸ. 17:15፤ ኢሳ. 5:26፤ 11:12፤ 13:2፤ መዝ. 20:5)፤ ይህ አሉታዊ ሊሆን ይችላል (ማለትም፣ ማምለጥ) ወይም አዎንታዊ (ማለትም፣ አንድጋ መሆን) ገለጻ።
2. እሱም ለማሳያ ፈልጎታል፣ ከእሱ ጋር ለመገናኘት (ማለትም፣ እውነትን፤ የዕብራይስጡ ተናባቢዎች ק–ט ፍቻቸው "ከቀስት" ወይም "እውነት" ሊሆን ይችላል፣ ቢዲቢ 905፤ የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት "ከቀስት" የሚለውን በ "ለ" ደረጃ ይደግፋል፣ (መጠነኛ ጥርጣሬ)፤ አየተመት፣ አኢመቅ፣ አእት መጽሐፍ ቅዱስ፤ የተእመቅ ምርጫውን ይደግፋሉ፣ ነገር ግን አኪጀት እና ጀፒኤስኦኤ "እውነት" የሚል አላቸው። "ቀስት" ለሚለው ቃል ተጨማሪ አናባቢ እዚህጋ ብቻ ነው ያለው።

ነጥቡ የሚሆነው ያህዌ አንዳንድ ድጋፍ ለእስራኤል እንደሚያደርግ ነው፣ በጦርነት ጊዜ ከእነርሱ ጋር በመገኘቱ።

**60፡4 "ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 3፡2 እና መግቢያ ለመዝሙር VII ላይ።

**60፡5 "ወዳጆችህ"** ይህ ቅጽል (ቢዲቢ 391) ለፍቅረኛ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ማኅልየ ማኅልይ ላይ (ማኅልየ ማኅልይ 1:2፤4፤ 4:10፤ 5:1፤ 7:13)። እዚህጋ ጥቅም ላይ የዋለው ለያህዌ የኪዳን ሕዝብ ነው (ኤር. 12፡7)። እሱም ብርቱ፣ ስሜት የሚነካ ገለጻ ነው።

▣ ይህ ቁጥር ሁለት የጸሎት ጥያቄዎች አሉት፣ 60፡4 ላይ በመመሥረት።
1. አድነን (ኤምቲ፤ ቁሬ "እኔን" – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል* ተተኳሪ፣ ማለትም፣ በድርጊትህ፣ መዝ. 3:7፤ 20:9
2. መልስልን (ኤምቲ፣ *ቁሬ* "እኔን") – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ *ቃል* ተተኳሪ

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ. 277) ለኤምቲ "እኛ" "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል (ሁነኛ ጥርጣሬ)። የብዙ ቁጥሩ ያለው ቁጥር 10 እና 11 ላይ ነው።

◘ **"ቀኝህ"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው የኃይልና የውጤታማ ድርጊት (ዘጸ. 15:6፤ መዝ. 17:7፤ 44:3፤ 98:1፤ 108:6፤ 138:7፤ 139:10፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝ. 7:3-4 ላይ)።

**መዝሙር ፡ 60፡6-8**

**6እግዚአብሔር በቅድስናው ተናገረ ደስ ይለኛል፥**
**ሴኬምንም እካፈላለሁ፥ የሱኮትንም ሸለቆ እሰፍራለሁ።**
**7ገለዓድ የእኔ ነው፥ ምናሴም የእኔ ነው**
**ኤፍሬም የራሴ መጠጊያ ነው።**
**ይሁዳ ንጉሤ ነው**
**8ሞዓብ መታጠቢያዬ ነው፥**
**በኤዶምያስ ላይ ጫማዬን እዘረጋለሁ**
**ፍልስጥኤም ይገዙልኛል።**

**60፡6-8** ይህ አንጓ የያህዌን ሉዓላዊነት ያከብራል (ወይም "ቅድስና፣" ቢዲቢ 871) በአሕዛብ ላይ (ዘዳ. 32፡8)። እነዚህ ቁጥሮች መዝ. 108፡7-14 ላይ ተደግመዋል፣ ማለትም፣ የአምልኮ ሥርዓት ክፍል እንደነበር። እሱም ሊያያዝ ይችላል ከዘጸ. 15፡14-17 ጋር። ያህዌ ራሱ ይናገራል (ማለትም፣ "እግዚአብሔር ተናግሯልና" — ቢዲቢ 180፣ ኬቢ 210፣ ፔይል የተጠናቀቀ)።

1. እደሰታለሁ – ቢዲቢ 759፣ ኬቢ 831፣ ቃል ተጓዳኝ
2. እካፈላለሁ – ቢዲቢ 323፣ ኬቢ 322፣ ፔል ተጓዳኝ
3. እሰፍራለሁ – ቢዲቢ 551፣ ኬቢ 547፣ ፔል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

4-5. "------------- የእኔ ነው"

6. "-------------- የራሴ መጠጊያዬ ነው"
7. "-------------- ንጉሤ ነው"
8. "------------ ላይ ጫማዬን እዘረጋለሁ" (ማለትም፣ የንቀት ፈሊጥ)
9. "------------ ይጮኻሉ፣ በእኔ ምክንያት" (ሊሆን የሚችለው፣ "በፍልስጥኤም ላይ እጮኻለሁ፣" የሚል ነው፣ እንደ መዝ. 108፡9ሐ)

የቦታ ስሞቹ ሁሉ በኢያሱ የነገዶች ሰፍራ ላይ እንደሆኑ ተገንዘብ።

1. አንድ ከተማ — ሴኬም
2. አንድ ሸለቆ — ሱኮት
3. አንድ ሰፍራ — ገለዓድ
4. ሦስት ነገዶች — ምናሴ፣ ኤፍሬም፣ ይሁዳ (ለይሁዳ እንደ በትረ-መንግሥት ዘፍ. 49፡10 ተመልከት)
5. ሦስት ተሸናፊ የከነዓን ሕዝቦች — ሞአብ፣ ኤዶም፣ ፍልስጥኤም

**መዝሙር ፡ 60፡9-12**

**9ወደ ጽኑ ከተማ ማን ይወስደኛል?**
**ማንስ እስከ ኤዶምያስ ይመራኛል?**
**10አቤቱ፥ የጣልኸን አንተ አይደለህምን?**
**አምላክ ሆይ፥ ከሠራዊታችን ጋር አትወጣም።**
**11በመከራችን ረድኤትን ስጠን**
**የሰውም ማዳን ከንቱ ነው።**
**12በእግዚአብሔር ኃይልን እናደርጋለን**
**እርሱ የሚያስጨንቁንን ያዋርዳቸዋልና።**

**60፡9-12** ይህ አንጓ የሚናገረው ወታደራዊ ድል ያለ ያህዌ ርዳታ እና መገኘት እንደማይቻል ነው (ማለትም፣ ቅዱስ ጦርነት)።

1. ቁጥር 9 ወታደራዊ ጥያቄ ይጠይቃል
2. ቁጥር 10 መንፈሳዊ እውነታን ያስረግጣል (ማለትም፣ ቅዱስ ጦርነት) ማለትም ያህዌ ከእስራኤል ሠራዊት ፊት ካልሄደ፣ ምንም ድል አይገኝም፣ መዝ. 44:9፤ 108:11
3. ቁጥር 11 አካላዊ እውነታን ያስረግጣል፣ ማለትም የሰዎች ወታደራዊ ድል ከንቱ እና ለአጭር ጊዜ መሆኑን
4. ቁጥር 12 ከያህዌ ጋር ብቻ ድል መኖሩን ያስረግጣል፣ ዘዳ. 20:1፤ 1 ሳሙ.17:45፣47፤ መዝ. 20:7፤ 22:16-17፤ 44:1-3፣5-7፤ 146:3፤ ዘካ. 4:6)። ይህም የሚጠቅሰው በእስራኤል የእግዚአብሔር የድል ዓላማ ከአሕዛብ አኳያ ነው፣ እንደ ድል አድራጊ ሳይሆን።

የእነዚህ ማስረገጫዎች አጠቃላይ ነጥብ የቁጥር 10 ጥያቄ ነው፣ "አምላክ ሆይ፣ የጣልከን አንተ አይደለኸምን?" እሱ ዕርዳታን ካልሰጠ ተስፋ አይኖርም (ቁ. 11ለ)። እሱ ካደረገ ድል ይኖራል (ቁ. 12)፣ ለሁለቱም ለእግዚአብሔር ዓላማ (ልዩ ርዕስ ተመልከት የመዝሙር 2 መግቢያ ላይ) እና ለእስራኤል ደኅንነትና ሰላም።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙሩን አንብበህ በፍሬ-ሐሳቦች፣ በርዕሶች ለመከፋፈል ሞክር። ቁ. 1-3 እና ቁ. 4-5 የተለያዩ ርዕሶች ይመስሉሃልን?
2. የቁጥር 6-8 *ሥነ-መለኮታዊ* ዓላማ ምንድነው? መዝሙር 108 ላይ ለምን ተደገመ?
3. ቁጥር 8 በርካታ አሉታዊ ምስያዎች አሉት። እነርሱን አብራራ
4. የቁጥር 9-12 ዋነኛ *ሥነ-መለኮታዊ* እውነት ምንድነው?

# መዝሙር 61
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንቀጽ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| በእግዚአብሔር ጥበቃ መተማመን<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ፤ በበገና። የዳዊት መዝሙር። | የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ጥበቃ ዋስትና | ለጥበቃ መጸለይ | ለጥበቃ መጸለይ | የስደት ጸሎት |
| 61:1-4 | | | | |
| | 61:1-2 | 61:1-2 | 61:1-2 | 61:1-2 |
| | 61:3-7 | 61:3-5 | 61:3 | 61:3-5 |
| | | | 61:4-5 | |
| 61:5-8 | | | | |
| | | 61:6-7 | 61:6-7 | 61:6-7 |
| | 61:8 | 61:8 | 61:8 | 61:8 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ በግልጽ ንጉሣዊ መዝሙር ነው (ዝከ. ቁ. 6) እግዚአብሔር ከንጉሥ ጋር እንዴት እንደሚሠራ ከሕዝቡ ጋር እንዴት እንደሚሠራ በውክልና ያሳያል (ዝከ. ቁ. 5)።

ለ. በመጀመሪያ፣ ቁጥር 2 የሚያመለክተው ስደትን ነው፣ ነገር ግን ቀሪው መዝሙር ይህንን አይደግፍም። ስለዚህ፣ ቁጥር 2ሀ ዘይቤአዊ መሆን ይኖርበታል፣ ለንጉሡ ስሜት መንፈሳዊ መነጠል።

ሐ. ይህ መዝሙር በርካታ የእግዚአብሔር የሚታወስ ምስሎች ይዟል።
1. ዓለት ከእኔ ከፍ የሚል
2. ለእኔ መሸሸጊያ ሆነህልኛል
3. የብርታት ማማ ሆነልኛል
4. በድንኳንህ ለዘላለም ልደር
5. በክንፎችህ ጥላ እጋረዳለሁ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 61፡1- 4**

**[1]አምላክ ሆይ፥ ልመናዬን ስማ፥**
**ጸሎቴንም አድምጥ።**
**[2]ልቤ ተስፋ በቈረጠ ጊዜ ከምድር ዳርቻ ወደ አንተ እጮኻለሁ**
**በድንጋይ ላይ ከፍ ከፍ አደረግኸኝ።**

> [3]ጽኑ ግንብ በጠላት ፊት
> ተስፋዬም ሆነኸኛልና መራኸኝ።
> [4]በድንኳንህ ለዘላለም እኖራለሁ
> በክንፎችህም ጥላ እጋረዳለሁ ሴላህ

**61፡1** ሁለት ተተኳሪ የጥያቄ ትይዩዎች ይህን መዝሙር ይጀምራሉ (መዝ. 86:6፤ ኢሳ. 28:23፤ 49:1፤ 51:4፤ ኤር. 18:19፤ ዳን. 9:19፤ ሆሴ. 5:1).

1. ጩኸቴን ስማ – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. ጸሎቴንም አድምጥ – ቢዲቢ 904፣ ኬቢ 1151፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

ቁጥር 2 ላይ መዝሙረኛው የሚለው፣ "ከምድር ዳርቻ ወዳንተ እጮኻለሁ" ነው። ይህም ድምጸቱ በስደት ላይ እንዳለ ሰው ጸሎት ሲሆን፣ ነገር ግን ቀሪው የመዝሙር ክፍል ይሄንን አይደግፍም። ስለዚህ፣ እሱ ለመነጠል ስሜት ምስያ መሆን ይኖርበታል፣ በእርሱ በኩል።

"ምድር" በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ "መሬት" በሚል ነው የሚረዳው (ማለትም፣ የተስፋይቱ ምድር)፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 1:2 ላይ። ቃላት ትርጉም የሚኖራቸው በዐውደ-ጽሑፍ ብቻ ነው!

ኤቢ ሐረጉን የሚረዳው ሲኦልን ለመጥቀስ ነው (ገጽ 84)። ይህም የተመሠረተው በኡጋሪታዊ ትይዩ ነው። እንደዚያ ከሆነ፣ መዝሙረኛው ሞትን ተጋፍጧል፣ መሰናክልን ሳይሆን።

▣ ***"መጮኽ"*** "መጮኽ" (ቢዲቢ 943) የደስታ ጩኸትን ሊያመለክት ይችላል፣ ወይም እንደዚህ የርዳታና የጥበቃ ጩኸት (መዝ. 17:1፤ 88:2፤ 106:44፤ 119:169፤ 142:6)።

**61፡2 "ከእኔ ከፍ ከፍ ባለ ድንጋይ"** "ዓለት" የሚለው መጠሪያ ሁለት የዕብራይስጥ ሥሮችን ያንጸባርቃል (ቢዲቢ 849 እና 700 I)። መጠሪያው በቅድሚያ (ቢዲቢ 849) የሚከሰተው ዘዳ. 32:4፣15፣18፣30፣31 ላይ ነው። እሱ እንዴት እንደሚገለጽ ተገንዘብ።

1. ዓለት – ዘዳ. 32:4፣15፣18፣30፣31
2. የማዳኑ ዓለት – ዘዳ. 32:15፤ 2 ሳሙ. 22:47፤ መዝ. 89:26፤ 95:1
3. የወለዳችሁ ዓለት – ዘዳ. 32:18
4. ዓለታቸው ሸጣቸው – ዘዳ. 32:30
5. ዓለታቸው እንደ እኛ ዓለት አይደለም – ዘዳ. 32:31
6. እንደ አምላካችን ያለ ዓለት የለምና – 1 ሳሙ. 2:2
7. ያህዌ ዓለቴ እና ምሽጌ እና አዳኜ ነው – መዝ. 18:2፤ 31:3፤ 71:3፤ 94:22
8. አምላኬ፣ ዓለቴ፣ የምሸሸግበት – መዝ. 18:2፤ 28:1፤ ኢሳ. 17:10
9. ከአምላካችን በቀር ዓለት ማነው – መዝ. 18:31
10. ያህዌ ሕያው ነው፣ ዓለቴም የተባረከ ይሁን – መዝ. 18:46
11. ዓለቴና አዳኜ –መዝ. 19:14
12. ዓለቴ (ቢዲቢ 700 I) – መዝ. 42:9
13. ዓለቴ በእርሱም ዓመጻ የሌለበት – መዝ. 92:15
14. በያህዌ የተባረከ፣ በዓለቴ – መዝ. 144:1
15. ያህዌ የዘላለም ዓለት – ኢሳ. 26:4
16. ወደ እግዚአብሔር ተራራ፣ ወደ እስራኤል ዓለት – ኢሳ. 30:29
17. ሌላ ዓለት አለ ወይ? – ኢሳ. 44:8

ቢዲቢ 700 I የሚከሰተው መዝ. 18:2፤ 42:9 ላይ ብቻ ነው። የጥሬ ፍችውም "ዓለታማ ገደል፣" ሲሆን ነገር ግን ከቢዲቢ 849 ጋር ተመሳሳይ ነው (ሁለቱም በመዝ. 18:2 ጥቅም ላይ ውለዋል)።

ይህ ምስያ በርካታ ታሳቢ መነሻ አለው።

1. የተራሮች መሠረቶች ወይም ከፍጥረት ጋር የተያያዙ ምሰሶዎች
2. ያህዌ ለእስራኤል ሕግን የሰጠበት ስፍራ
3. ሞሪያ ተራራ ላይ ያለ መቅደስ
4. የአካላዊ ተራሮች ብርታትና ጽኑነት
5. ተራሮች ከፍተኛ ጫፍ ናቸው፣ ወደ ሰማይ የቀረቡ፣ አምላክ ወደሚኖርበት

▣ **"ከእኔ ከፍ ያለ"** ይህ ብዙ ነገር ማለት ሊሆን ይችላል።

1. ደኅንነትና መጠጊያ የሚሰጥ ዓለት፣ መዝሙረኛው ለራሱ መስጠት የማይችለውን
2. እሱ ሊወጣው የማይችለው ዓለት ወይም ሊገነዘበው የማይችለው (ማለትም፣ የእግዚአብሔር ጽኑዕነት)
3. የእግዚአብሔር ከፍ ያለ ስፍራና መዝሙረኛው ያለበት የውድቀት ስፍራ (ማለትም፣ ልቤ ተስፋ በቆረጠ ጊዜ)

LXX እና ፔሺታ "በዓለቱ ላይ ተውከኝ" የሚል አላቸው።

**61፡3** አብዛኛው ምናብ እግዚአብሔርን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለው ወታደራዊ ፍችዎች አሉት።

1. ከጋሻ ጋር የሚያያዝ መጠጊያ 2 ሳሙ. 22:31፤ መዝ. 18:31፤ ምሳ. 30:5
2. ከምሽግ ጋር የተያያዘ መጠጊያ መዝ. 59:16
3. እዚህጋ መጠጊያው የተያያዘው "ከብርታት ግንብ" ጋር ነው (ምሳ. 18:10) መዝ. 62:7፣ "የብርታቴ ዓለት"

**61፡4** ቁጥር 4 ሁለት ተጓዳኝ ግሦች አሉት።

1. በድንኳንህ ልደር – ቢዲቢ 157፣ ኬቢ 184፣ *ቃል ተጓዳኝ*፣ መዝ. 27:5፤ 31:20፤ 32:7
2. በክንፎችህ ጥላ እጋረዳለሁ – ቢዲቢ 340፣ ኬቢ 337፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡11-12)

ቁጥር 3 ወታደራዊ ምናብ እንዳለው፣ ቁጥር 4 ከመቅደስ ወይም ከ"ዓለት" ሊያያዝ የሚችል ምስያ አለው ቁ. 2 ላይ። የቁ. 4ሀ ምስያ ደግሞ መዝ. 23:6፤ 27:4 ላይ ይገኛል።

"ዘላለም" የሚለው ቃል የብዙ ነው፣ እሱም ለጽንሰ-ሐሳቡ አጽንዖት የሚሰጥ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9:5 ላይ)። እኔ እንደማስበው በብኪ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ ዐውድ ላይ እሱ የሚገልጸው ደስተኛ፣ ረጅም ሕይወት በመቅደስ ኅብረት ላይ ያለውን ነው (ማለትም፣ ድንኳን) ከያህዌ ጋር (መዝ. 23:6)።

◘ **"በክንፎችህ ጥላ እጋረዳለሁ"** ይህ አንስታይ የእግዚአብሔር ምስያ ነው፣ እንደ ጠባቂ እናቲት ወፍ (ማቴ. 23:37፤ ሉቃስ 13:34)። መዝ. 17:8 ላይ ማስታወሻ ተመልከት እንዲሁም ልዩ ርዕስ መዝ. 5:11-12 ላይ።

◘ **"ሴላህ"** መዝ. 3:2 ላይ ያለውን ማስታወሻ እና መግቢያ ለመዝሙር፣ VII ተመልከት።

### መዝሙር ፡ 61:5- 8

**5አቤቱ፥ አንተ ስእለቴን ሰምተሃልና**
**ስምህንም ለሚፈሩ ርስትህን ሰጠሃቸው።**
**6ለንጉሥ ከቀን በላይ ቀን ትጨምራለህ፥**
**ዓመታቱም ከትውልድ ወደ ትውልድ ይሆናሉ።**
**7በእግዚአብሔር ፊት ለዘላለም ይኖራል**
**ይጠብቁት ዘንድ ምሕረትንና እውነትን አዘጋጅለት።**
**8እንዲሁ ለስምህ ለዘላለም እዘምራለሁ**
**ስእለቴን ሁልጊዜ እፈጽም ዘንድ።**

**61:5-8** ይህ አንጓ የሚዛመደው ከንጉሥ ጋር ነው፣ እንደ ያህዌ የኪዳን ሕዝቦች ተወካይ።
1. ንጉሡ ስእለት ተስሏል (ማለትም፣ የእምነት ተስፋዎች) ለያህዌ።
2. ያህዌ ለእርሱ/እስራኤል ምድር ሰጥቷል (ማለትም፣ ርስት፣ ዘፍ. 15:12-21) የከነአንን ለሚፈሩት።
3. ያህዌ የንጉሡን ሕይወት ያራዝማል (ንጉሣዊ ግነታዊ ዘይቤ እንደሆነ ተመልከት)።
4. ንጉሡ በእግዚአብሔር ፊት በዙፋኑ ለዘላለም ይቀመጣል ("ዘላለም" ዘላለማዊ አለመሆኑ ግልጽ ነው፣ ነገር ግን ረጅም ዘመን እንጂ)። የአኪን የዳበረ ሥነ-መለኮት ተመልሰህ በዕብራይስጥ ቃላት እንዳታነብ ተጠንቀቅ (ንጉሣዊ ግነታዊ ዘይቤ)።
5. ያህዌ ያደርጋል (ቢዲቢ 584፣ ኬቢ 599፣ ፒል ተተኳሪ፣ የጸሎት ጥያቄ) ቸርነት እና እውነት (ሰውኛ ወኪሎች፣ መዝ. 40:11፤ 57:3፤ 89:14፣ "መልካምነት እና ምሕረት" መዝ. 23:6 ላይ፣ "ብርሃን" እና "እውነት" መዝ. 43:3 ላይ)። ይኸው ተመሳሳይ ጽንሰ-ሐሳብ ምሳ. 20:28 ላይ ተመልክቷል። ንጉሥን መደገፍ እስራኤልን መደገፍ ነው።

**61:5** ኒዶቲ ቅጽ 2፣ ገጽ 531 መልካም አስተያየት አለው "ስምህን ለሚፈሩ" ለሚለው። እነርሱ የሚወክሉት ታማኝ ተከታዮችን ነው (መዝ. 15:4፤ 25:12፣14፤ 103:11፣13፤ 118:4)። ኒዶቲ በመጠኑ ለየት ያሉ መልኮች ዝርዝርን ይጨምራል።
1. የሚፈሩህ – መዝ. 31:19
2. የሚፈሩት – መዝ. 34:7
3. ስምህን የሚፈሩ – መዝ. 61:5
4. እግዚአብሔርን የሚፈሩ – መዝ. 66:16

**61:8** እግዚአብሔር ለንጉሡና ለእስራኤል ካለው መልካምነት የተነሣ፣ ንጉሡ ምስጋና ይዘምራል (ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ፒል ተጓዳኝ) ለእርሱ።

እንደገናም የ"ዘላለም" አጠቃቀም መታየት የሚኖርበት እንደ ረጅም፣ ስኬታማ አገዛዝ ዘይቤ ነው። የእንጉሡ የእምነት ተስፋዎች ("ስእለቶች") ተከብረዋል፣ ተከናውነዋል፣ እንዲሁም ተፈጽመዋል በመቅደስ። ይህ ሐረግ ከመዝ. 30:13 ጋር ተመሳሳይ ነው፣ እዚያም የተደራጀ የአምልኮ ሥርዓትን ይጠቅሳል (ማለትም፣ የምስጋና መሥዋዕት) ወይም የአምልኮ ሥርዓት (ከመሥዋዕት ማቅረብ ጋር የተያያዘ፣ መዝ. 7:17)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ግለሰባዊ ኀዘን ነው ንጉሣዊ ኀዘን?
2. "ከምድር ዳርቻ" የሚለውን ሐረግ አብራራ። ጸሐፊው በስደት ነበርን?
3. ቁጥር 4 ዘላለማዊ ሕይወትን ያመለክታልን? (ዝከ. ቁ. 7) ይህ መሢሐዊ መዝሙር ነውን?
4. "ስእለት"ን አብራራ፣ በዚህ መዝሙር ጥቅም ላይ በዋለበት መልኩ። (ዝከ. ቁ. 5፣8)

# መዝሙር 62
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| አምላክ ብቻ ከተንኮለኛ መሸሸጊያ ነው <u>ኤምቲ መግቢያ</u> ለመዘምራን አለቃ፤ ስለ ኤዶታም የዳዊት ዝማሬ | የእግዚአብሔርን ማዳን በጸጥታ የመጠበቅ ውሳኔ | በእግዚአብሔር ጥበቃ መተማመን | በእግዚአብሔር ጥበቃ መተማመን | በእግዚአብሔር ብቻ ተስፋ ማድረግ |
| 62:1-2 | 62:1-2 | 62:1-2 | 62:1-2 | 62:1-2 |
| 62:3-4 | 62:3-4 | 62:3-4 | 62:3-4 | 62:3-4 |
| 62:5-8 | 62:5-7 | 62:5-7 | 62:5-7 | 62:5-7ለ |
| | | | | 62:7c-8 |
| | 62:8 | 62:8 | 62:8 | |
| 62:9-10 | 62:9-10 | 62:9-10 | 62:9-10 | 62:9 |
| | | | | 62:10 |
| 62:11-12 | 62:11-12 | 62:11-12 | 62:11-12 | 62:11-12 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 62፡1-2**
**1ነፍሴ ለእግዚአብሔር የምትገዛ አይደለችምን?**
**መድኃኒቴ ከእርሱ ዘንድ ናትና።**
**2እርሱ አምላኬ መድኃኒቴም ነውና**
**እርሱ መጠጊያዬ ነው፥ እጅግም አልታወክም።**

**62፡1-2** ይህ አንጓ የሚገልጸው መዝሙረኛው በጸጥታ የሚጠብቀውን አምላክ ነው (ቁ. 1-2 ከቁ. 5-6 ጋር ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ እንደሆነ ተገንዘብ)። እሱ በትዕግሥት እግዚአብሔርን ጠብቋል፣ ለእርሱ ብሎ እንዲሠራ (መዝ. 131፡2)።
1. ደኅንነቱ ከእግዚአብሔር ነው (ቢዲቢ 447)፣ ቁ. 1
2. እግዚአብሔር ብቻ ነው ዐለቱ (ቢዲቢ 849)፣ ቁ. 2፣6፣ መዝ. 61:2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት
3. እግዚአብሔር ብቻ ነው ደኅንነቱ፣ ቁ. 2፣6
4. እግዚአብሔር ነው ምሽጉ፣ ቁ. 2

ከዚህ አምላክ የተነሣ፣ አይናወጥም (ቢዲቢ 556፣ ኬቢ 555፣ ኒፋል ያልተጠናቀቀ፣ ዝከ. ቁ. 6)። ቁጥር 1 ላይ ያለው ሐረግ ቁጥር 6 ላይ ተደግሟል ነገር ግን ቁጥር 1 "በታላቅ" የሚል ቃል ይጨምራል። አእቅ፣ አየተመት፣ እና ጂፒኤስኦኤ የሚተረጉሙት "ፈጽሞ" በሚል ነው።

**62፡1 "ብቻ"** ይህ ተውሳከ ግሥ (ቢዲቢ 36) በመጀመሪያ የሚከሰተው ቁጥር 1፣2፣4፣5፣6፣10 ላይ ነው፣ ለአጽንዖትና ለጽሑፋዊ ዘዴ መዝሙሩን አንድ ላይ ለማያያዝ። ታማኝ የሕይወት ስልት እና ኃጢአተኛ የሕይወት ስልት የማይገናኝ ነው (ዝከ. 62፡4፣9)።

ጂፒኤስኦኤ እሱን የሚተረጉመው "በርግጥ" በሚል ነው።

▣ **"ነፍስ"** ይህ ነፍሽ *nephesh* (ቢዲቢ 659) ሙሉውን ሰው ይገልጻል። መዝ. 13፡2 እና 16፡9 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

**መዝሙር ፡ 62፡3-4**

[3]እስከ መቼ በሰው ላይ ትቆማላችሁ?
እናንተ ሁላችሁ እንዳዘነበለ ግድግዳ እንደ ፈረሰም ቅጥር
ትገድላላችሁ።
[4]ነገር ግን ከብሬን ይሽሩ ዘንድ መከሩ፥
ሐሰትንም ይወድዳሉ
በአፋቸው ይባርካሉ፥
በልባቸውም ይረግማሉ። ሴላህ።

**62፡3-4** ይህ አንጓ የሚገልጸው ያልታመኑ ጠላቶችን ነው።

1. በጠበኝነት ይጮኻሉ (መጮኽ) – ቢ.ዲ.ቢ. 223፣ ኬ.ቢ. 243፣ *ፖለል* ያልተጠናቀቀ፣ የብዙ፤ ይህ ግሥ በብኪ የሚገኘው እዚህጋ ብቻ ነው፣ ትርጉሙም የመነጨው ከዓረብኛ ሥር ነው
2. ለመግደል ይሞክራሉ (መበታተን) – ቢ.ዲ.ቢ. 953፣ ኬ.ቢ. 1283፣ *ፑኣል* ያልተጠናቀቀ፤ አእቅ መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው ፔል ነው፣ "እናንተ ሁላችሁ ነፍሰ-ገዳዮች ናችሁ" (ገጽ 927)
3. እነርሱ ዓይነታቸው (በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ቁ. 3ሐ አላቸው፣ መዝሙረኛውን የሚያመለክቱ፤ አየተመት፣ አእቅ፣ አኢ.መቅ፣ ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ)
   ሀ. ያዘነበለ ግድግዳ – ቢ.ዲ.ቢ. 639፣ ኬ.ቢ. 692፣ *ቃል* ተገብሮ አንቀጽ
   ለ. የፈረሰ ቅጥር – ቢ.ዲ.ቢ. 190፣ ኬ.ቢ. 218፣ *ቃል* ተገብሮ አንቀጽ
4. ይመክራሉ (ቢ.ዲ.ቢ. 419፣ ኬ.ቢ. 421፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) ሌላው ከፍ ካለ ማዕርጉ እንዲወድቅ በመግፋት – ቢ.ዲ.ቢ. 632፣ ኬ.ቢ. 673፣ *ሂፊል*ያልተወሰነ አወቃቀር
5. ሐሰትንም ይወድዳሉ – ቢ.ዲ.ቢ. 953፣ ኬ.ቢ. 1280፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
6. ይባርካሉ (ቢ.ዲ.ቢ. 138፣ ኬ.ቢ. 159፣ *ፔል* ያልተጠናቀቀ) በአፋቸው፣ ነገር ግን በልባቸው ይረግማሉ – ቢ.ዲ.ቢ. 886፣ ኬ.ቢ. 1103፣ *ፔል* ያልተጠናቀቀ፤ አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ያዕቆብ 3:10 ከዚህ መዝሙር መጥቶ ከሆነ

በፍሬአቸው (ማቴ. 7:16-20) እና በቃላቸው (ማቴ. 12:34-37) ታውቋቸዋላችሁ።

**መዝሙር ፡ 62፡5-8**

[5]ነገር ግን፥ ነፍሴ ሆይ፥ አንቺ ለእግዚአብሔር ተገዢ፥
ተስፋዬ ከእርሱ ዘንድ ናትና።
[6]እርሱ አምላኬ መድኃኒቴም ነውና
እርሱ መጠጊያዬ ነው አልታወክም።
[7]መድኃኒቴና ክብሬ በእግዚአብሔር ነው
የረድኤቴ አምላክ ተስፋዬም እግዚአብሔር ነው።
[8]የሕዝብ ማኅበር ሁላችሁ፥ በእርሱ ታመኑ፥
ልባችሁንም በፊቱ አፍስሱ
እግዚአብሔር ረዳታችን ነው። ሴላህ።

**62፡5-8** የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ ቁጥሮች በትክክል እንደ 62፡1-2 ዓይነት ናቸው። መዝሙረኛው ድርጊቶቹን ይገልጻል እንደ ታማኝ ተከታይ፣ ከማይታመኑ ተከታዮች ጋር በማወደዳር።

1. እሱ በእግዚአብሔር ማዳንና ክብር ላይ *ዐርፏል* ("ክብር፣" ቢ.ዲ.ቢ. 458)
2. እሱ በእግዚአብሔር ላይ ዐርፏል (ይታሰባል) እንደ ዓለቱና ብርታቱ
3. እሱም እግዚአብሔርን መጠጊያው አድርጓል

ቁጥር 8 ከአንድ ግለሰብ ትኩረት ወደ ወል (የሁሉም) ትኩረት ተቀይሯል (በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች የተለየ አንጓ ያደርጉታል)። እሱም የሚጀምረው በሁለት ተተኳሪዎች ነው፣ ወደ ታማኝ ተከታዮች ማኅበረሰብ በማመልከት።

1. ሁልጊዜ በእርሱ ታመኑ – ቢ.ዲ.ቢ. 105፣ ኬ.ቢ. 120፣ *ቃል* ተተኳሪ፣ መዝ. 37:3፣5፤ 52:8፤ ኢሳ. 26:4. ጠንከር የሚለው ክፍል "ሁልጊዜ፣" የሚለው ሐረግ ነው ነገር ግን እሱ በርግጠኛ ሰላም እና መተማመን ቁልፍ ነው (መዝ. 34:1)።
2. ልባችሁን በፊቱ አፍስሱ – ቢ.ዲ.ቢ. 1049፣ ኬ.ቢ. 1629፣ *ቃል* ተተኳሪ፣ 1 ሳሙ. 1:15፤ ሰቆ. 2:19 (ማለትም፣ ስለ ስሜቶቻችሁና ችግሮቻችሁ ታማኞች ሁኑ በእግዚአብሔር ፊት በምትጸልዩበት ጊዜ፤ ይህም ፈጽሞ የተለየ ነው ቁጥር 1 እና 2 ላይ ካለው "ጸጥታ"። ቁጥር 1 እና 5 እግዚአብሔርን ይጠብቃሉ ከጸሎት በኋላ እንዲሠራ፣ እንዲሁም ቁጥር 8 የጸሎት ጥሪ ነው።)
3. እግዚአብሔር መጠጊያችን ነው — እግዚአብሔር የግለሰቦች ብቻ የደኅንነት ምንጭ/ስፍራ አይደለም፣ የማኅበረሰቡም የደኅንነት የእምነት ምንጭ/ስፍራ እንጂ!

◘ **"ሴላህ"** መዝ. 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፤ ደግሞም መግቢያ ለመዝሙር VII።

**62፡5 "ለእግዚአብሔር"** ቁጥር 1 ላይ ይህ ትርጉም ልክ ነው ነገር ግን እዚህ ተጨማሪ መነሻ *ላሜድ* አለ (መስተጻምር ሳይሆን)፣ እሱም "እግዚአብሔር ራሱ" ለሚለው አጽንዖት የሚሰጥ።

◘ "ጸጥ በሉ" የሚለው መስተጻምር (ቢ.ዲ.ቢ. 198፣ ኬ.ቢ. 226፣ *ቃል* ተተኳሪ) እዚህጋ ጥቅም ላይ የዋለው ስሙ ባለበት ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 189) ቁጥር 1 ላይ ጥቅም ላይ የዋለ።

**መዝሙር ፡ 62፡9-10**

[9]ነገር ግን የሰው ልጆች ከንቱ ናቸው፥ የሰው ልጆችም ሐሰተኞች ናቸው
በሚዛንም ይበድላሉ፥
እነርሱስ በፍጹም ከንቱ ናቸው።
[10]ዓመፃን ተስፋ አታድርጉ፥
ቅሚያንም አትተማመኑት
ባለጠግነት ቢበዛ ልባችሁ አይከራ።

**62፡9-10** ይህ አንጓ ሰዎችን ሁሉ ይመለከታል፣ ከተለያዩ የኅብረተሰብ ደረጃዎች (ማለትም፣ ዝቅተኛ ደረጃ... ማዕርግ)። በእግዚአብሔር ላይ ካለ እምነት/መታመን በቀር እነርሱ ከንቱ ናቸው (ቢዲቢ 210 I) እና ውሸት (ቢዲቢ 469)። ኤምቲ "የሰው ልጆች" የሚል አለው፣ ሁለት ጊዜ። ትርጉሞቹ "ዝቅተኛ ደረጃ" እና "ማዕርግ" የሚሉ ይሆናሉ፣ መዝ. 49፡2 ካለው ተመሳሳይ ሐረግ። ጄፒኤስኦኤ "የሰው ልጆች ከንቱ ናቸው፤ ሚኞች (ቢዲቢ 35)፣ ከንቱ፣" እሱም ከመዝ. 49፡2 ጋር ያለውን መያያዝ እንደ ትይዩ የማይቀበል፣ ብሎም "የአዳም ልጆች" ቢዲቢ 9) እና "ከንቱ ልጆች" የሚለውን የሰው ልጆችን ሁሉ እንደሚጠቅስ የሚያመለክት። ለእኔ የሚመስለኝ ቁ. 10 የሚያመለክተው ድሀ እና አቅም የሌለው በእስራኤል ባላባት ወገኖች መጨቆናቸውን ነው፣ እናም መዝሙር 49 የተሻለ ትይዩ ይሆናል።

ሁለተኛው ዓረፍተ ነገር የንግድ ሚዛኖችን ምስያ ይጠቀማል። በዕብራውያን ከበድ የሚለው የከበረ/ዋጋ ያለው ነው፤ ማለትም ቀለል ያለው (ማለትም፣ እስትንፋስ፣ ቢዲቢ 210 I ሁለቴ ጥቅም ላይ ውሏል) ክብር የሌለው ነው።

ቁጥር 10 ሦስት ተጽዕኖዎች አሉት፣ እምነተ-ቢስ ተከታዮችን የሚያመለክቱ።

1. በጭቆና አትተማመኑ – ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ አሉታዊ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. በዝርፊያ አትተማመኑ – ቢዲቢ 211፣ ኬቢ 236፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ አሉታዊ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. ባለጠግነት ቢበዛ ልባችሁ አይኩራ – ቢዲቢ 1011፣ ኬቢ 1483፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ አሉታዊ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

በዚህ አንጓ ላይ እና 62፡4 ላይ በመመሥረት፣ የሚመለከታቸው ሰዎች የእስራኤል ባላባት ወገን ናቸው (ማለትም፣ ሲቪል፣ ወታደራዊ፣ ነጋዴ)።

**62፡9 "ከንቱ... እስትንፋስ"** እነዚህ ሁለቱም የዕብራይስጥ ቃል ትርጉሞች ናቸው (ቢዲቢ 210 I)። ይህም ከመክብብ ሁለት ቁልፍ ቃላት አንደኛው ነው። የእኔን ማስታወሻ ተመልከት፣ በቃል ላይ መክ. 1፡2 ላይ በኢንተርኔት መስመር www.freebiblecommentary.org ላይ።

**መዝሙር ፡ 62፡11-12**

[11]እግዚአብሔር አንድ ጊዜ ተናገረ፥
እኔም ይህን ብቻ ሰማሁ
ኃይል የእግዚአብሔር ነው፥
[12]አቤቱ፥ ምሕረትም ያንተ ነው
አንተ ለእያንዳንዱ እንደ ሥራው ፍዳውን ትሰጣለህና።

**62፡11-12** ይህ የመጨረሻ አንጓ የሚመለከተው ሥነ-መለኮታዊ ጉዳይ ጻድቅ እንዴት እንደሚከናወንለት (እንደሚሳካለት) ነው (ኢዮብ፤ መዝሙር 37 እና 73)። የሙሴ ሕግ የሚያስረግጠው ብልጽግና፣ ጤንነት፣ እና ስኬት ለኪዳን ታዛዥነት ነው (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)። *"ሁለቱ መንገዶች"* (መዝሙር 1፤ ዘዳ. 30፡15፣19) ደግሞ የሚያስረግጠው ተመሳሳይ ነው። ሆኖም፣ በተጨባጭ፣ ዘወትር ባለጸጎች በዝባዦች፣ ስስታሞች፣ ጨካኞች፣ ክፉ ጨቋኞች ናቸው፣ እነርሱም የውድቀት አስተሳሰብን በሥጋ የሚወክሉ ናቸው፡ ሁሉም ነገር ለእኔ ብቻ፣ እንደምንም ብሎ!

ፍትሐዊ ባልሆነ ዓለም ነው የምንኖረው። እግዚአብሔር ሊያስተካክለው ቃል ገብቷል። የፍርድ ቀን አለ። አንድ ቀን የዘራነውን እናጭዳለን (ኢዮብ 34፡11፤ መዝ. 28፡4፤ ምሳ. 24፡12፤ መክ. 12፡14፤ ኤር. 17፡10፤ 32፡19፤ ማቴ. 16፡27፤ 25፡31-46፤ ሮሜ. 2፡6፤ 14፡12፤ 1 ቆሮ. 3፡8፤ 2 ቆሮ. 5፡10፤ ገላ. 6፡7-10፤ 2 ጢሞ. 4፡14፤ 1 ጴጥ. 1፡17፤ ራዕ. 2፡23፤ 20፡12፤ 22፡12)! በዚህ ዙሪያ የረዳኝ መጽሐፍ የሀናህ ዊዛል ስሚዝ *"የክርስቲያን ምሥጢር ሊደስተኛ ሕይወት"* ነው።

**62፡11** ይህ ዘይቤ ነው በጣም ለታወቀውና ዘወትር ለሚጠቀሰው እውነት በሦስት ክፍሎች (ማለትም፣ ኃይል፣ የኪዳን ታዛዥነት፣ እና ሽልማት)። በውድቀት ምክንያት አንዳንድ ሰዎች የያህዌን ኃይል ይለማመዳሉ፤ አንዳንዶች ቸርነቱን! ድርጊቶቻችን አባታችን ማን እንደሆነ ያሳያሉ!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ቁጥር 1 እና 5 ከቁጥር 8 እንዴት ይለያሉ?
2. ቁጥር 3ሐ ማንን ነው የሚያመለክተው?
3. ቁጥር 8 የተለየ (ራሱን የቻለ) አንጓ ለምን ሆነ?
4. ቁጥር 9 ማንን ነው የሚመለከተው? እሱስ ከመዝ. 49፡2 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
5. እግዚአብሔር የተናገራቸውን ነጥቦችና መዝሙረኛው ብዙ ጊዜ የሰማቸውን ዘርዝር።

# መዝሙር 63
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የታመነች ነፍስ በአምላክ ትረካለች<br>ኤምቲ መግቢያ __የዳዊት መዝሙር በይሁዳ ምድረ በዳ በነበረበት ጊዜ | ደስታ ከእግዚአብሔር ጋር ባለ ኅብረት | ከግል ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት | እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ | እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረግ |
| 63:1-5 | 63:1-2 | 63:1-4 | 63:1-5 | 63:1-2 |
| | 63:3-5 | | | 63:3-5 |
| 63:6-8 | | 63:5-8 | | |
| 63:9-11 | 63:6-8 | | 63:6-8 | 63:6-8 |
| | 63:9-11 | 63:9-11 | 63:9-11 | 63:9-11 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ባሰገራሚ ሁኔታ ይህ መዝሙር ምንም ተተኳሪ፣ ተጽዕኖዊ፣ ወይም ተጓዳኝ የለውም።

ለ. ይህ መዝሙር ሌሎችን አያስጠነቅቅም፣ ነገር ግን ግለሰባዊ ፍለጋ ለጥልቅ፣ ለግላዊ ግንኙነት፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚሆን ይገልጻል (መዝ. 42፡1-4)።

ሐ. እንደ ሌሎቹ በርካታ መዝሙራት ከጠላቶች ጋር የመቃረን ገጽታ አለ (ዝከ. ቁ. 9-11)። በቁጥር 11 ምክንያት፣ ይህ የሚያንጸባርቀው የንጉሥን ሐሳብ ነው፣ ስለዚህ እነርሱ ሊሆኑ የሚችሉት
   1. ባዕዳን
   2. እምነተ-ቢስ እስራኤላውያን

መ. ቁጥር 11ሀ ይሄንን ወዲያውኑ ንጉሣዊ መዝሙር አያደርገውም፤ 63፡9-11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፣ ለአማራጭ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 63፡1-5**
**1አምላኬ፥ አምላኬ፥ ወደ አንተ እገሠግሣለሁ**
**ነፍሴ አንተን ተጠማች፥ ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች**
**እንጨትና ውኃ በሌለበት በምድረ በዳ።**
**2ኃይልህንና ክብርህን አይ ዘንድ**

**እንዲሁ በመቅደስ ውስጥ ተመለከትሁህ።**
**3ምሕረትህ ከሕይወት ይሻላልና**
**ከንፈሮቼ ያመሰግኑሃል።**
**4እንዲህ በሕይወቴ ዘመን አመሰግንሃለሁ፥**
**በአንተም ስም እጆቼን አነሣለሁ።**
**5ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች፥**
**ከንፈሮቼም ስምህን በደስታ ያመሰግናሉ።**

**63፡1-5** በዚህ አንጓ መዝሙረኛው ስለ እግዚአብሔር ምን እንደሚሰማው ይገልጻል (ቁ. 1፣ ኤሎሂም እና ኤል፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡1 ላይ)።

1. በብርቱ ይፈልገዋል ("በማለዳ ይመለከተዋል") – ቢ.ዲ.ቢ 1007፣ ኬቢ 1465፣ ፒኤል ያልተጠናቀቀ (መዝ. 78:34፤ መዝ. 7:15፤ 8:17፤ 13:24፤ ኢሳ. 26:9፤ ሆሴ. 5:15)፤ ተመሳሳይ ሥር ስም ዓይነት የሚሆነው "ማለዳ" (መዝ. 57:8)
2. ነፍሱ (ኔፍሽ፣ ቢ.ዲ.ቢ 659) እግዚአብሔርን ተጠማች – ቢ.ዲ.ቢ 854፣ ኬቢ 1032፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 42:2፤ 84:2፤ ማቴ. 5:6
3. ሥጋው (ቢ.ዲ.ቢ 142) በብርቱ ትናፍቃለች ("ዛለች") እግዚአብሔርን – ቢ.ዲ.ቢ 484፣ ኬቢ 480፣ ቃል የተጠናቀቀ፤ እዚህጋ ብቻ በብኪ፤ ከዓረብኛ ሥር "የፊት መገርጣት"
4. እሱም መጠማቱን እና መዛሉን በደረቅ እና በአስቸጋሪ ስፍራ በመሆኑ ምክንያት እንደሆነ ይገልጻል፣ ምንም ውኃ በሌለበት (መዝ. 143:6)፤ እግዚአብሔር ዘወትር ይገለጻል፣ "የሕይወት ውኃ" ምንጭ እንደሆነ (ኢሳ. 12:3፤ 44:3፤ 55:1፤ ኤር. 2:13፤ 17:13፤ ዮሐንስ 4:10፤ 7:37-38፤ ራዕ. 21:6፤ 22:17)

የእግዚአብሔር ብርቱ ፍለጋው፣ በደረቅ ምድር የተፈጠረው ቀደም ብሎ በሚያውቀው የሚያድስ ደስታ ነው፣ በመቅደስ በአምልኮ ጊዜ (ቁ. 2)።

1. እነሆ እግዚአብሔር በመቅደሱ ("በቅድስናው፣" መዝ. 60:6፤ 89:35፤ 102:19) – ቢ.ዲ.ቢ 302፣ ኬቢ 301፣ ቃል የተጠናቀቀ፤ ይህ ቃል ሊል የሚችለው መቅደስ ነው ነገር ግን በሁኔታው ያንን ማለቱ ላይሆን ይችላል፤ ይህ የግጥም ስንኝ በግዞት ያለ ሰውን የሚመለከት አይመስለኝም፤ ኤቢ (ገጽ 97) ይልቁንም የሚለው "ሰማያዊ መቅደስ" ነው ቁ. 5 ላይ እና "የዘላለም ሕይወት" ቁ. 4 ላይ
2. ኃይሉን ተመልከቱ – ቢ.ዲ.ቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ ቃል ያልተወሰነ አወቃቀር፣ መዝ. 59:17፤ 62:11
3. ክብሩን ተመልከቱ — ቢ.ዲ.ቢ የላይኛው ግሥ ይመስላል (ድርብ ባለቤት)

ኃይልና ክብር እንዴት እንደተገጡ በትክክል አልተቀመጠም ነገር ግን "ክብር" የሚለው ቃል ለሼኪናህ (የክብር ደመና) እስከዋለ ድረስ (ማለትም፣ ደመና) በምድረ በዳ መንከራተት ጊዜ (ዘጸ. 16:7፣10፤ 24:16፣17፤ 40:34፣35፤ ሌዋ. 9:6፣23፤ ዘኍ. 14:10፤ 16:19፤ 17:7፣10፤ 20:6)፤ እንደ 1 ነገ. 8:11 ያለ ነገር በድጋሚ ተከስቶ ሊሆን ይችላል (ሌለኛው አማራጭ የሚሆነው የእግዚአብሔር የራሱ ራዕይ ነው፣ እንደ ኢሳይያስ 6 ወይም ሕዝቅኤል 1፤ 10)።

**63፡3-5** እነዚህ ቁጥሮች የሚገልጹት መዝሙረኛው እንዴት እግዚአብሔርን እንደሚያመሰግን ነው፣ ስለ ቸርነቱ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7) ከሕይወት ይበልጣል።

1. ከንፈሮቹ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ – ቢ.ዲ.ቢ 986 II፣ ኬቢ 1387፣ ፒኤል ያልተጠናቀቀ
2. በሕይወት ዘመኑ ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናል – ቢ.ዲ.ቢ 138፣ ኬቢ 159፣ ፒኤል ያልተጠናቀቀ
3. እጆቹን ያነሣል – ቢ.ዲ.ቢ 669፣ ኬቢ 724፣ ቃል ያልተጠናቀቀ
4. ነፍሱ ትጠግባለች – ቢ.ዲ.ቢ 959፣ ኬቢ 1302፣ ቃል ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 36:8
5. አፉ ምስጋናን ያቀርባል፣ በደስታ ከንፈሮች – ቢ.ዲ.ቢ 237 II፣ ኬቢ 248፣ ፒኤል ያልተጠናቀቀ

**63፡4 "እጆችን ማንሣት"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 28፡2 ላይ።

▣ **"በስምህ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ስም መዝ. 5፡11-12 ላይ።

## መዝሙር ፡ 63፡6-8

**6በመኝታዬም አስብሃለሁ፥**
**በማለዳም እናገርልሃለሁ**
**7ረዳቴ ሆነኸኛልና፥**
**በክንፎችህም ጥላ ደስ ይለኛልና።**
**8ነፍሴ በኋላህ ተከታተለች፥**
**እኔንም ቀኝህ ተቀበለችኝ።**

**63፡6-8** ይህ አንጓ የመዝሙረኛውን ነጸብራቅ ይቀጥላል፣ ስለ እግዚአብሔር መልካምነትና ክብካቤ።

1. ተኝቶ እግዚአብሔርን ያስባል – ቢ.ዲ.ቢ 269፣ ኬቢ 269፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ ዘዳ. 6:6-9፤ መዝ. 119:15፣ 48፣97፣99፤
2. በምሽትም እግዚአብሔርን ይማልዳል – ቢ.ዲ.ቢ 211 I፣ ኬቢ 237፣ ቃል ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 4:4
3. እግዚአብሔር ረዳት ሆኖታል (ቢ.ዲ.ቢ 740 I) – ቢ.ዲ.ቢ 224፣ ኬቢ 243፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 27:9
4. እሱ ተጠብቋል (በእግዚአብሔር ክንፎች ጥላ ሥር) እናም በደስታ ይዘምራል – ቢ.ዲ.ቢ 943፣ ኬቢ 1247፤ ፒኤል ያልተጠናቀቀ
5. እሱ (ነፍስ) ከእግዚአብሔር ጋር ተጣብቋል – ቢ.ዲ.ቢ 179፣ ኬቢ 209፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ ዘፍ. 2:24፤ ሩት 1:14፤ 2 ነገ. 18:6
6. የእግዚአብሔር ቀኝ ተቀብላዋለች – ቢ.ዲ.ቢ 1069፣ ኬቢ 1751፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 18:35፤ 41:12

ቁ. 5 እና 6 እንዴት ሁለቱንም ወገን የኪዳን ግንኙነት እንደሚያንጸባርቁ ተገንዘብ። እሱም በሁለቱም በእግዚአብሔር እና በሰው ዘንድ ያለውን ምርጫና ድርጊት ያነሣል።

**63፡7 "በክንፎችህም ጥላ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 17፡8 ላይ እና ልዩ ርዕስ መዝ. 5፡11-12 ላይ።

**63፡8 "ቀኝህ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 18፡35 ላይ እና ልዩ ርዕስ፡ እጅ መዝ. 7፡3-4 ላይ።

**መዝሙር ፡ 63፡9-11**

**9 እነርሱ ግን ነፍሴን ለከንቱ ፈለጓት**
**ወደ ምድር ጥልቅ ይገባሉ።**
**10 ለሰይፍ እጅ አልፈው ይሰጣሉ፥**
**የቀበሮም እድል ፈንታ ይሆናሉ።**
**11 ንጉሥ ግን በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል**
**በእርሱ የሚምል ሁሉ ይከብራል፥**
**ሐሰትን የሚናገር አፍ ይዘጋልና።**

**63፡9-11** በመዝሙራት ላይ አዘውትሮ እንደሚሆነው፣ አንጓው የሚመለከተው የመዝሙረኛውን ጠላቶች ነው። በዚህ ላይ "ንጉሥ" ተለይቶ ተመልክቷል። ይህም ሊሆን የሚችለው

1. ንጉሡ መዝሙረኛው መሆኑን
2. መዝሙረኛው ንጉሡ የገጠመውን ችግሮች መግለጹን እና ንጉሡ ምን እንደሚሰማው ማወቁን መግለጹን ነው (ዝኪ. ቁ. 11ሀ)
3. እሱ የጽሑፍ ጥበብ ነው፣ ግለሰባዊ መዝሙራትን ከወል መዝሙራት ጋር ለማያያዝ (ዝኪ. ቁ. 11ለ)

እነዚህ መግለጫዎች ስለ ጠላቶች ናቸው (ማለትም፣ ሕይወቱን ሊያጠፉት የሚሹት እና ብሎም እስራኤልን)።

1. ወደ ምድር ጥልቅ ውስጥ ይገባሉ (ማለትም፣ ጉድጓድ፣ ሲኦል፣ መቃብር፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡6 ላይ)።
   በብኪ ሰዎች ሁሉ ወደ ሲኦል ይወርዳሉ፣ ሰዎች ሁሉ ወደ ሀደስ (የሙታን ስፍራ) በአኪ እንደሚሄዱ፣ የፍርድ ቀንን ለመጠበቅ። እሱም ሊሆን የሚችለው "ዝቅተኛው ስፍራ" የሚወክለው የእምነት-የለሾች ተከታዮች እና የጣዖት አምላኪዎችን ማደሪያ ስፍራ ነው።
2. እነርሱም ለሰይፍ ኃይል አልፈው ይሰጣሉ – ቢዲቢ 620፣ ኬቢ 669፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*
3. ለቀበሮች ዕድል-ፈንታ ይሆናሉ (ማለትም፣ ተገቢ ቀብር አያገኙም)
4. ሐሰትን የሚናገር አፍ ይዘጋል – ቢዲቢ 698፣ ኬቢ 55፣ *ኒፋል ያልተጠናቀቀ*

በዚህም ምክንያት

1. ንጉሥ በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
2. በእርሱ የሚምል ሁሉ (ቢዲቢ 989፣ ኬቢ 1396፣ *ኒፋል አንቀጽ*) ይከብራል – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ *ሂዝፔል ያልተጠናቀቀ*፣ ኢሳ. 48፡1፤ 65፡16

ትክክል እና እውነት እና እምነት በመጨረሻ ይገናል፣ በአምላካችን ባሕርይና ዓላማ ምክንያት!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ከመዝሙር 42 ጋር እንዴት ይመሳሰላል?
2. መዝሙረኛው በስደት ላይ ነውን? ለምን ወይስ ለምን አልሆነም?
3. ቁጥር 2ለ ወደ ምንድነው የሚያመለክተው?
4. ቁጥር 3-5 የት እንደተከሰተ ታስባለህ?
5. የቁጥር 9-10 ጠላቶች እነማናቸው?
6. ይህ ንጉሣዊ መዝሙር ነውን? ለምን ወይስ ለምን አልሆነም?

# መዝሙር 64
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጸሎት ከድብቅ ጠላቶች ለመዳን<br><br>ኤምቲ መግቢያ ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር። | በክፉዎች መጨቆን ግን በጌታ መደሰት | ጸሎት ከግል ጠላቶች ለመጠበቅ | ጸሎት ለመጠበቅ | የተሳዳቢዎች ቅጣት |
| 64:1-6 | 64:1-4 | 64:1-6 | 64:1-6 | 64:1-2 |
| | | | | 64:3-4 |
| 64:7-10 | 64:5-6 | | | 64:5-6 |
| | 64:7-9 | 64:7-9 | 64:7-10 | 64:7-8 |
| | | | | 64:9 |
| | 64:10 | 64:10 | | 64:10 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙረኛው ተቸግሯል በምሥጢር ጠላቶች። ይህም እስራኤላዊ ወዳጆቹን ያመለክታል። እነርሱም ተጠርተዋል
1. ጠላት፣ ቁ. 1 (ቢዲቢ 33፤ ኬቢ 38፣ *ቃል* ቦዝ አንቀጽ)
2. ክፉ አድራጊዎች፣ ቁ. 2 (ቢዲቢ 949፤ ኬቢ 1269፣ *ሂፊል* ቦዝ አንቀጽ)
3. በደልን የሚያደርጉ፣ ቁ. 2 (ቢዲቢ 821፣ ኬቢ 950፣ *ቃል* ቦዝ አንቀጽ)

ለጠላቶች ስሞች ማስታወሻ ተመልከት፣ 1:5፤ 5:10፤ 15:2-5 ላይ።

ለ. ድርጊታቸው (ቁ. 2-6) ተዘርዝሯል።
1. ፍርሃትን ይፈጥራሉ (ቢዲቢ 808)፣ መዝ. 91:5
2. ምሥጢራዊ ምክርን ያካሂዳሉ
3. በደልን ይፈጽማሉ
4. እንደ ሰይፍ የተሳለ አንደበት አላቸው
5. ንግግራቸውን እንደ ቀስት ያልማሉ
6. አሸምቀው ያጠቃሉ
7. አይፈሩም (ማለትም፣ እግዚአብሔርን)
8. በክፉ ዕቅዳቸው ጽኑ ናቸው
9. ወጥመድ በስውር ለማስቀመጥ ያቅዳሉ
10. እንደተሸሸጉ ያስባሉ (ማለትም፣ ከእግዚአብሔር)
11. ፍትሕን ለማዛባት ያቅዳሉ

12. እጅግ የታሰበበት ተንኮል አላቸው
13. እነርሱ በሐሳባቸውና በልባቸው ክፉ ናቸው

ሐ. የእግዚአብሔር ድርጊት በእነርሱ ላይ ተቆርጧል
1. በቀስት ይወጋቸዋል
2. እንዲሰናከሉ ያደርጋቸዋል
3. የገዛ ራሳቸውን ቃል በእነርሱ ላይ ለፍርድ ይጠቀማል
4. እፍረትን እንዲለብሱ ያደርጋቸዋል
5. የእርሱ ድርጊት በእነርሱ ላይ፣ ለሰዎች ሁሉ ምክንያት ይሆናል
   ሀ. ፍርሃት/አክብሮት
   ለ. ሥራውን ይገልጻል
   ሐ. ድርጊቶቹን ያመላክታሉ
6. የእርሱ ድርጊት ለጻድቅ ሰው ምክንያት ይሆናል
   ሀ. በድርጊቱ እንዲደሰቱ
   ለ. እንዲታመን (ማለትም፣ መታመን) በእርሱ
   ሐ. በልባቸው ያከብራሉ

መ. የሰው ንግግር፣ ባርኮት ወይም ርግማን ሊሆን ይችላል (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 52፡2 ላይ)።

ሠ. ምንም እንኳ ታሪካዊ መቼቱን ለማስረገጥ ወይም መዝሙረኛውን መለየት ባይቻልም፣ ምን ያህል ወታደራዊ ምስያዎች ጥቅም ላይ መዋላቸው አስገራሚ ነው።
1. ሰይፍ
2. ቀስት
3. ሽምቅ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 64፡1-6**

**1አቤቱ፥ ወደ አንተ በለመንሁ ጊዜ ጸሎቴን ስማኝ፥**
**ከጠላትም ፍርሃት ነፍሴን አድን።**
**2ከክፉዎች ሸንጎ**
**ከዓመፀኞችም ብዛት ሰውረኝ።**
**3እንደ ሰይፍ ምላሳቸውን አሰሉ**
**መራራ ነገርን ለማድረግ፥**
**4ንጹሕንም በስውር ለመንደፍ ቀስትን ገተሩ**
**ድንገት ይነድፉታል አይፈሩምም።**
**5ለእነርሱ ለራሳቸው ክፉ ነገርን አጸኑ**
**ወጥመድን ይሰውሩ ዘንድ ተማከሩ**
**ማንስ ያየናል? ይላሉ።**
**6ዓመፃን ፈልጓት፥**
**ሲፈትኑም አለቁ**
**የሰው የውስጥ አሳቡና ልቡ የጠለቀ ነው፥**

**64፡1 "ስማ"** በርካታ አንጓዎች መዝሙራት ላይ በተተኳሪዎች ነው የሚተዋወቁት (መዝ. 17:1፤ 27:7፤ 28:2፤ 30:10፤ 39:12፤ 54:2፤ 61:1፤ 64:1፤ 84:8፤ 102:1፤ 119:149፤ 130:2፤ 143:1)። መዝሙራቱ ዘወትር ለእግዚአብሔር ጸሎት ናቸው፣ እሱን የሚለምኑ፣ ለሕዝቡ ወይም ለጻድቅ ተከታዩ እንዲያደርግ።

ጸሎት አስደናቂ ዕድል ነው ለእግዚአብሔር ሕዝብ። እሱም ኃይልን ወደ ምድር ይለቃል፣ ቀደም ሲል ያልነበረውን። ከታች ሦስት ልዩ ርዕሶችን አኑሬአለሁ፣ በመጽሐፍ ቅዱሳዊ የተለያዩ የጸሎት ገጽታዎች ላይ።

### ልዩ ርዕስ፡ ውጤታማ ጸሎት

ሀ. አንዱ በሦስትነቱ አንድ አምላክ ከሆነው ጋር ባለው ግላዊ ግንኙነት ይያያዛል
1. ከአብ ፍቃድ ጋር ይያያዛል
   ሀ. ማቴ. 6፡10
   ለ. 1 ዮሐንስ 3፡22
   ሐ. 1 ዮሐንስ 5፡14-15

2. በኢየሱስ የሚኖር
   ዮሐንስ 15፡7
3. በኢየሱስ ስም የሚጸልይ
   ሀ. ዮሐንስ 14፡13፤14
   ለ. ዮሐንስ 15፡16
   ሐ. ዮሐንስ 16፡23-24
4. በመንፈስ የሚጸልይ
   ሀ. ኤፌ. 6፡18
   ለ. ይሁዳ 20

ለ. ከአንዱ የግል ውስጣዊ ሐሳብ ጋር ይያያዛል
1. የማያወላውል
   ሀ. ማቴ. 21፡22
   ለ. ያዕቆብ 1፡6-7
2. በተሳሳተ መለመን - ያዕቆብ 4፡3
3. በግለኝነት መለመን - ያዕቆብ 4፡2-3

ሐ. ከአንዱ የግል ምርጫዎች ጋር ይያያዛል
1. ጽናት
   ሀ. ሉቃስ 18፡1-8
   ለ. ቆላስያስ 4፡2
   ሐ. ያዕቆብ 5፡16
2. በቤት ባለ አለመግባባት
   1 ጴጥሮስ 3፡7
3. ኃጢአት
   ሀ. መዝሙር 66፡18
   ለ. ኢሳይያስ 59፡1-2
   ሐ. ኢሳይያስ 64፡7

ጸሎት ሁሉ መልስ ያገኛል፣ ነገር ግን ጸሎት ሁሉ ስኬታማ አይደለም። ጸሎት የሁለትዮሽ ግንኙነት ነው። እግዚአብሔር ሊያደርግ የሚችለው የከፋ ነገር ለአማኞች ተገቢ ያልሆነ ጥያቄ ምላሽ መስጠት ነው።

## ልዩ ርዕስ፡ የምልጃ ጸሎት

I. መግቢያ

ሀ. ጸሎት አስፈላጊ ነው በኢየሱስ ምሳሌነት ምክንያት
1. የግል ጸሎት፣ ማርቆስ 1:35፤ ሉቃስ 3:21፤ 6:12፤ 9:29፤ 22:29-46
2. መቅደሱን ለማጥራት፣ ማቴ. 21፡13፤ ማርቆስ 11፡17፤ ሉቃስ 19፡46
3. ምሳሌያዊ ጸሎት፣ ማቴ. 6፡5-13፤ ሉቃስ 11፡2-4

ለ. ጸሎት የግል እምነታችንን ወደ ተጨባጭ ድርጊት የሚወስድ፣ ወደ እግዚአብሔር ሕላዌ፣ ፍቃድ የሚያደርስ ነው፣ እናም በእኛ በኩልም ሆነ በሌሎች ለመሥራት ያስችላል፣' በጸሎታችን በኩል።

ሐ. እግዚአብሔር ራሱን በአካል ያስገኛል፣ በብዙ ስፍራዎች የልጆቹን ጸሎት ሰምቶ ድርጊት ለማከናወን (ያዕቆብ 4፡2)።

መ. ዋነኛው የጸሎት ዓላማ የእኛ ከእግዚአብሔር ጋር ያለ ኅብረትና ጊዜ መስጠት ነው።

ሠ. የጸሎት ወሰኑ ምንም ነገርና ማንም ነው፣ አማኞችን የሚገዳቸው። አንድ ጊዜ ልንጸልይ እንችላለን፣ በእምነት፣ ወይም ደግመን ደጋግመን እንጸልያለን፣ ሐሳቡ ወይም ግዳችን እስከተመለሰ።

ረ. ጸሎት ብዙ ነገሮችን ሊነካ ይችላል።
1. ምስጋናና ጸሎት ለሥላሴ (አምላክ) ማቅረብ
2. ለእግዚአብሔር ምስጋና ማቅረብ ስለመገኘቱ፣ ኅብረቱ፣ እና ሰጪነቱ
3. ኃጢአተኝነታችንን ለመናዘዝ፣ ሁለቱንም ያለፈውንም ሆነ የአሁኑን
4. አስፈላጊ ለመሰሉን ፍላጎቶች ወይም መሻቶች ልመና
5. በአብ ፊት ለሌሎች ለመማለድ ባስፈለገበት ጊዜ

ሰ. የምልጃ ጸሎት ምሥጢራዊ ነው። እግዚአብሔር በጣም የምንጸልይላቸውን፣ ከእኛ ይልቅ ይወዳቸዋል፣ የእኛ ጸሎት በለውጥ፣ በምላሽ፣ ወይም በመሻት፣ በእኛ ብቻ ሳይሆን በእነሱም ላይ ተጽዕኖ ቢኖረውም።

II. መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነገሮች

ሀ. ብሉይ ኪዳን
1. ስለ ምልጃ ጸሎት ጥቂት ምሳሌዎች።
   ሀ. አብርሃም ስለ ሰዶም ማለደ፣ ዘፍ. 18፡22
   ለ. ሙሴ ለእስራኤል ጸለየ
      (1) ዘጸዓት 5፡22-23

(2) ዘጸዓት 32፡31
(3) ዘዳግም 5፡5
(4) ዘዳግም 9፡18፣25

ሐ. ሳሙኤል ለእስራኤል ጸልዮአል

(1) 1ኛ ሳሙኤል 7፡5-6፣ 8-9
(2) 1ኛ ሳሙኤል 12፡16-23
(3) 1ኛ ሳሙኤል 15፡11

መ. ዳዊት ለልጁ፣ 2ኛ ሳሙኤል 12፡16-18

2. እግዚአብሔር የሚማልዱ ይፈልጋል፣ ኢሳይያስ 59፡16።
3. የታወቀ፣ ያልተናዘዙት ኃጢአት ወይም ጸጸት የሌለበት አዝማሚያ ጸሎታችንን ይጎዳዋል።

ሀ. መዝሙር 66፡18
ለ. ምሳሌ 28፡9
ሐ. ኢሳይያስ 59፡1-2፤ 64፡7

ለ. አዲስ ኪዳን

1. የወልድና የመንፈስ ቅዱስ የምልጃ አገልግሎት

ሀ. ኢየሱስ

(1) ሮሜ 8፡34
(2) ዕብራውያን 7፡25
(3) 1ኛ ዮሐንስ 2፡1

ለ. መንፈስ ቅዱስ፣ ሮሜ 8፡26-27

2. የጳውሎስ የምልጃ አገልግሎት

ሀ. ለአይሁድ መጸለይ

(1) ሮሜ 9፡1
(2) ሮሜ 10፡1

ለ. ለአብያተ ክርስቲያናት ጸልዮአል

(1) ሮሜ 1፡9
(2) ኤፌሶን 1፡16
(3) ፊሊጵስዩስ 1፡3-4፣9
(4) ቆላስይስ 1፡3፣9
(5) 1ኛ ተሰሎንቄ 1፡2-3
(6) 2ኛ ተሰሎንቄ 1፡11
(7) 2ኛ ጢሞቴዎስ 1፡3
(8) ፊሊሞና፣ ቁ. 4

ሐ. ጳውሎስ አብያተ ክርስቲያናት ለእሱ እንዲጸልዩ ጠይቋል

(1) ሮሜ 15፡30
(2) 2ኛ ቆሮንቶስ 1፡11
(3) ኤፌሶን 6፡19
(4) ቆላስይስ 4፡3
(5) 1ኛ ተሰሎንቄ 5፡25
(6) 2ኛ ተሰሎንቄ 3፡1

3. የቤተክርስቲያን የምልጃ አገልግሎት

ሀ. አንዱ ለአንዱ መጸለዩ

(1) ኤፌሶን 6፡18
(2) 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡1
(3) ያዕቆብ 5፡16

ለ. ለተለዩ ወገኖች የተጠየቀ ጸሎት

(1) ጠላቶቻችን፣ ማቴ. 5፡44
(2) ክርስቲያን ሠራተኞች፣ ዕብራውያን 13፡18
(3) ገዥዎች፣ 1ኛ ጢሞቴዎስ 2፡2
(4) ለታመመ፣ ያዕቆብ 5፡13-16
(5) ወደ ኃጢአቱ ለተመለሰ፣ 1ኛ ዮሐንስ 5፡16

III. ጸሎትን የሚያሰናክሉ

ሀ. ከክርስቶስና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር ያለን ግንኙነት

1. በእሱ ኑሩ፣ ዮሐንስ 15፡7
2. በስሙ፣ ዮሐንስ 14:13፣14፤ 15:16፤ 16:23-24
3. በመንፈስ፣ ኤፌሶን 6፡18፤ ይሁዳ 20
4. እንደ እግዚአብሔር ፍቃድ፣ ማቴዎስ 6:10፤ 1 ዮሐንስ 3:22፤ 5:14-15

ለ. የውስጥ ሐሳቡ

1. ባለማወላወል፣ ማቴዎስ 21፡22፤ ያዕቆብ 1፡6-7
2. ትሕትናና ንስሐ፣ ሉቃስ 18፡9-14
3. በተሳሳተ መለመን፣ ያዕቆብ 4፡3
4. ራስ ወዳድነት፣ ያዕቆብ 4፡2-3

ሐ. ሌሎች ገጽታዎች

1. መጽናት
   ሀ. ሉቃስ 18፡1-8
   ለ. ቆላስይስ 4፡2
2. መጠየቅን መቀጠል
   ሀ. ማቴዎስ 7፡7-8
   ለ. ሉቃስ 11፡5-13
   ሐ. ያዕቆብ 1፡5
3. በቤት ስምምነት ማጣት፣ 1ኛ ጴጥሮስ 3፡7
4. ከታወቀ ኃጢአት ነጻ መሆን
   ሀ. መዝሙር 66፡18
   ለ. ምሳሌ 28፡9
   ሐ. ኢሳይያስ 59፡1-2
   መ. ኢሳይያስ 64፡7

IV. ሥነ-መለኮታዊ ማጠቃለያ

ሀ. እንዴት መታደል ነው። እንዴት ያለው አጋጣሚ ነው። እንዴት ያለው ተግባርና ኃላፊነት ነው

ለ. ኢየሱስ ምሳሌያችን ነው። መንፈስ መሪያችን ነው። አብ በጉጉት እየጠበቀ ነው።

ሐ. እናንተን ሊለውጥ ይችላል፣ ቤተሰባችሁን፣ ጓደኞቻችሁን፣ እና ዓለምን።

## ልዩ ርዕስ፡ ጸሎት፣ ያልተወሰነ ሆኖም የተወሰነ

ሀ. ቀዳሚዎቹ ሦስቱ ወንጌላት

1. አማኞች በጸሎት እንዲጸኑ ይበረታታሉ፣ እግዚአብሔርም "መልካም ነገሮችን" ይሰጣል (ማቴዎስ) ወይም "መንፈሱን" (ሉቃስ) ማቴ. 7:7-11፤ ሉቃስ 11:5-13)
2. በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት ዐውደ-ጽሑፍ አማኞች (ሁለት) በጸሎት እንዲተባበሩ ይበረታታሉ (ማቴ. 18፡19)
3. በይሁዲነት ፍርድ ዐውደ-ጽሑፍ አማኞች በእምነት ያለ ጥርጥር መጠየቅ አለባቸው (ማቴ. 21:22፤ ማርቆስ 11:23-24)
4. በሁለቱ ምሳሌዎች ዐውደ-ጽሑፍ (ቁ. 1-8፣ ዓመጸኛው ዳኛ እና ቁ. 9-14፣ ፈሪሳዊውና ኃጢአተኛው) አማኞች ይበረታታሉ ተለይተው እንዲያከናውኑ፣ ከክፉው ዳኛ እና ራሱን ካጸደቀው ፈሪሳዊ። እግዚአብሔር ትሑቱንና ንስሐ የገባውን ይሰማል (ሉቃስ 18፡1-14)

ለ. የዮሐንስ ጽሑፎች

1. ዕውር ሆኖ በተወለደውና ኢየሱስ በፈወሰው ሰውዬ ዐውደ-ጽሑፍ፣ እውነተኛው የፈሪሳውያን ዕውርነት ተገልጧል። የኢየሱስ ጸሎት (እንደ ሌላው) ምላሽ አግኝቷል፣ እግዚአብሔርን በማወቁና በፍቃዱ በመኖሩ ሳቢያ (ዮሐንስ 9፡31)።
2. የዮሐንስ የደርቡ ቤት ገለጻ (ዮሐንስ 13-17)
   ሀ. 14፡12-14 —የእምነት ጸሎት ባሕርዩ
      1) ከአማኞች ይመጣል
      2) በኢየሱስ ስም ይጠየቃል
      3) እግዚአብሔር እንዲከብርበት ይሻል
      4) ትእዛዛትን ይጠብቃል (ቁ. 15)
   ለ. 15፡7-10 — የአማኞች ጸሎት ባሕርዩ
      1) በኢየሱስ ይኖራል
      2) የእርሱ ቃልም በእነርሱ ይኖራል
      3) እግዚአብሔር እንዲከበርበት ይሻል
      4) ብዙ ፍሬ ያፈራል
      5) ትእዛዛትን ይጠብቃል (ቁ. 10)
   ሐ. 15፡15-17 — የአማኞች ጸሎት ባሕርዩ
      1) መመረጣቸው
      2) ፍሬ በማፍራታቸው
      3) በኢየሱስ ስም መጸለይ
      4) እርስ በርስ በመዋደድ ትእዛዙን ማክበር
   መ. 16፡23-24 — የአማኞች ጸሎት ባሕርዩ
      1) በኢየሱስ ስም ይቀርባል

2) ደስታው ሙሉ እንዲሆን መሻት
3. የዮሐንስ የመጀመሪያው መልእክት (1 ዮሐንስ)
ሀ. 3፡22-24 — የአማኞች ጸሎት ባሕርዩ
1) ትእዛዛቱን መጠበቅ (ቁ. 22፤24)
2) በአግባቡ መኖር
3) በኢየሱስ ማመን
4) እርስ በርስ መዋደድ
5) በእርሱ መኖር እርሱም በእኛ
6) የመንፈስ ቅዱስ ስጦታ መኖር
ለ. 5፡14-16 — የአማኞች ጸሎት ባሕርዩ
1) በእግዚአብሔር መተማመን
2) እንደ ፍቃዱ
3) አማኞች ለእርስ በርሳቸው ይጸልያሉ
ሐ. ያዕቆብ
1. 1፡5-7 — በብዙ መከራዎች የሚያልፉ አማኞች ጥበብን እንዲለምኑ ተጠርተዋል፣ ያለ መጠራጠር
2. 4፡2-3 — አማኞች በተገቢው ሐሳብ መጠየቅ ይኖርባቸዋል
3. 5፡13-18 — የጤና ችግር ያለባቸው አማኞች ይበረታታሉ
ሀ. ሽማግሌዎች እንዲጸልዩላቸው እንዲጠይቁ
ለ. የእምነት ጸሎት ያድናል
ሐ. ኃጢአታቸው ይቅር እንዲባል መጸለይ
መ. ኃጢአታቸውን እርስ በርስ መናዘዝ እና አንዱ ለአንዱ መጸለይ (ከ1 ዮሐንስ 5፡16 ጋር ተመሳሳይ)
ለውጤታማ ጸሎት ቁልፉ ክርስቶስን መምሰል ነው። ይህ ነው በኢየሱስ ስም መጸለይ ማለት። እግዚአብሔር ለብዙዎች ክርስቲያኖች የሚያደርገው የከፋ ነገር ለግለኛ ጸሎታቸው ምላሽ መስጠት ነው! በአንድ በኩል ጸሎት ሁሉ ምላሽ አግኝቷል። እጅግ ዋጋ ያለው የጸሎት ገጽታ፣ አማኙ ከእግዚአብሔር ጋር ጊዜ ማሳለፉ ነው፣ እግዚአብሔርን በማመን።

⊡

**አአመመቅ፣ አየተመት** **"ደጅ መጥናት"**
**አኪጀት** **"መማለድ"**
**LXX** **"ልመና"**

ስሙ (ቢዲቢ 967) ዘወትር በቅኔ ጥቅም ላይ ይውላል "ደጅ ለመጥናት።"

1. ኢዮብ 7:11፤ 9:27፤ 10:1፤ 21:4፤ 23:2
2. መዝሙር 55:2፤ 142:2
3. ምሳ 23:29

መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር ያመለክታል፣ ስለ ሕይወት ኢ-ፍትሐዊነት፣ ከወዳጅ የኪዳን ሰዎች በተያያዘ ጥቃት።

⊡ **"ከጠላትም ፍርሃት ነፍሴን አድን።"** ግሡ (ቢዲቢ 665 1፣ ኬቢ 718፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) ጥቅም ላይ የዋለው "ከ" ከሚለው መስተጻምር ጋር ነው መዝ. 12:7፤ 32:7፤ 140:1፣4 ላይ። እሱም እሱም ጥቅም ላይ የዋለው ለእግዚአብሔር ጥበቃ፣ ክብካቤ፣ ወይም ከለላ ነው ዘዳ. 32:10፤ መዝ. 25:20፤ 31:23፤ 40:11፤ ኢሳ. 26:3፤ 42:6፤ 49:8 ላይ። የእግዚአብሔር ሕዝብ ማመን ይገባዋል፣ እግዚአብሔር እንደሚጠብቀው። ይህ ማለት ሕይወት ያለ ችግር ይሆናል ማለት አይደለም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ርግጠኛ መገኘት ግርማ የተሞላው ምሕረቱን፣ በሚፈልጉት ላይ ለማሳየት ነው።

⊡ **"ጠላት"** ቃሉ የነጠላ ነው ነገር ግን በወል (ብዙ) መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው (ዝከ. ቁ. 2-6)።

**64፡2** "መደበቅ" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 711፣ ኬቢ 771፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*) የ "መጠበቅ" ትይዩ ነው ቁጥር 1 ላይ። መዝሙረኛው በሌሎች የኪዳን ተካፋዮች እንደተበደለ አስቧል፣ እነርሱም የእርሱን ሞት በምሥጢር ያቀዱ።

መዝሙረኛው ያህዌን እንዲደብቀው መጠየቁን ተገንዘብ፣ ነገር ግን ክፉዎች ምሥጢራዊ ዕቅዳቸውን ደብቀዋል፣ እሱን ለማጥፋት (ዝከ. 64፡5)።

⊡

**አአመመቅ** **"ብጥብጥ"**
**አኪጀት** **"ዓመጽ"**
**አየተመት** **"ተንኮል "**
**አእቅ፣ የተእመቅ** **"ሁከት"**
**አኢመቅ** **"ዓመጸኞች"**
**ጀፒኤስአኤ** **"ሸንጎ"**

ይህ ሥር ሦስት ጊዜ ብቻ ነው ብኪ ላይ የሚከሰተው። እሱም አዓአቅ ላይ የተተረጎመው እንደ

1. መዝ. 2፡1 — "ማሴር"
2. መዝ. 55፡15 —"የሰዎች ስብስብ"
3. መዝ. 64፡2 — "የታወከ ሸንጎ"

**64፡4 "ያለ ነውር"** ቃሉ (ቢዲቢ 1070) የሚገልጸው የሞራል ንጽሕናን ነው፣ ኃጢአት-የለሽ ሰውን ሳይሆን (ማለትም፣ ሳይታወቅ፣ ሆን ተብሎ ያልተሠራ ኃጢአት)። እሱም ለኢዮብ ጥቅም ላይ ውሏል (ዝኪ. 1፡1፣8፤ 2:3፤ 8:20፤ 9:20-22፤ መዝ. 37:37)። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 18:20-24 ላይ።

**64:5**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ለእነርሱ ለራሳቸው ክፉ ነገርን አጸኑ"** |
| **አኪጀት** | **"እነርሱ ለክፉ ነገር ራሳቸውን አጸኑ"** |
| **አየተመት** | **"እነርሱ ከክፉ ዓላማቸው ጋር በጥብቅ ተያያዙ"** |
| **አእቅ** | **"እነርሱ በክፉ ተንኮላቸው እርስ በርሳቸው ተበረታቱ"** |
| **አኢመቅ** | **"እነርሱ በክፉ ተንኮላቸው እርስ በርሳቸው ተደጋገፉ"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"እነርሱ ለራሳቸው በክፉ ቃል ናቸው"** |
| **የተእት** | **"እነርሱ ለራሳቸው ክፉ ውሳኔአቸውን አጸኑ"** |

ኒዶቴ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 72፣ በርካታ ታሳቢ ፍችዎችን/ትርጉሞችን ዘርዝሯል፣ ለፔይል ከግሡ (ቢዲቢ 304፣ ኬቢ 302)።

1. አጥብቆ መያዝ
2. እነርሱ በራሳቸው  አበረቱ (ማለትም፣ የጋራ ድጋፍ)
3. እነርሱ በራሳቸው አጸኑ (ማለትም፣ ክፉ ዓላማቸውን አጸኑ)

▣ **"ማን ያያቸዋል"** ይህ ሐረግ የሚያመለክተው

1. ምሥጢራዊ ዕቅዳቸውን ነው፣ መዝሙረኛውን ለማጥመድ
2. አለማመናቸውን፣ እግዚአብሔር የሚያውቀውን፣ በመዝሙረኛውም በኩል የሚያደርገውን ሥራ  (ኢዮብ 22:13፤ መዝ. 10:11፤ 59:7፤ 94:7፤ ኢሳ. 29:15፤ ሕዝ. 8:12)

**64:6** ቁጥር 6 ላይ ሦስት ቃላት አሉ፣ የዕብራይስጥን ፊደል የሚጋሩ፣ ሠፓበ (ቢዲቢ 344)።

1. መመርመር (አአመመቅ፣ "ማመንጨት")
2. ባግባቡ የታሰበበት
3. ሴራ

▣ **"የሰው የውስጡ ሐሳብና ልቡ ጥልቅ ነው"** ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ ይህ የሚያመለክተው የመዝሙረኛውን ጠላቶች ክፉ ሐሳብ ነው። ቢዲቢ "ጥልቅ" በሚል ይገልጸዋል (ቢዲቢ 771) "ተፈልጎ እንደማይገኝ" (ኢዮብ 12:22፤ መክ. 7:24 [ሁለቴ]) ወይም ምሥጢራዊ። አኢመቅ እና መልኅቅ መጽሐፍ ቅዱስ እሱን የሚተረጉሙት፣ ያህዌ ድርጊታቸውን እንደሚያውቅ ለመግለጽ ነው። ሆኖም፣ እሱ የሚመስለው ቁጥር 1-6 ስለ ጠላት ድርጊቶች ነው፣ እንዲሁም ቁጥር 7-9 ስለ ያህዌ ምላሽ ነው።

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 282-284) የሚያሳየው በርካታ ጽሑፋዊ ጉዳዮችንና ታሳቢዎችን ነው፣ በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች ላይ። አብዛኞቹ "ሐ" ደረጃ አላቸው (ምክንያታዊ ጥርጣሬ)።

## መዝሙር ፡ 64፡7-10

7 **እግዚአብሔርም ከፍ ከፍ ይላል።**
**የድንገትም ፍላጻ ያቈስላቸዋል**
8 **አንደበታቸው ያሰናክላቸዋል፥**
**የሚያዩአቸውም ሁሉ ይደነግጣሉ።**
9 **ሰዎች ሁሉ ፈሩ፥**
**የእግዚአብሔርንም ሥራ ተናገሩ፥**
**ሥራውንም አስተዋሉ።**
10 **ጻድቅ በእግዚአብሔር ደስ ይለዋል፥ በእርሱም ይታመናል**
**ልባቸውም የቀና ሁሉ እልል ይላሉ።**

**64፡7** ይህ ሁነኛ የሥራ መገልበጥ ምስያ ነው። ኃጢአተኛ በጻድቅ ላይ ያደረገው (ዝኪ. ቁ. 3-4) አሁን በራሱ ላይ ሆነበት።

ይኸው ተመሳሳይ ምስያ ቁጥር 8ን ያብራራል። ክፉ አሳቢዎች እነርሱም በመዝሙረኛው ላይ የጥላቻ ቃላትን የሚጠቀሙ፣ አሁን የገዛ ራሳቸውን ቃላት በራሳቸው ላይ ተጠቀሙ።

**64:8 "ራስ መነቅነቅ"** ይህ የመደነቅ እና የመናቅ ፈሊጥ ነው (መዝ. 22:7፤ 44:14፤ ኤር. 18:16፤ 48:27፤ ሰቆ. 2:15)።

**64፡9** የያህዌን ድርጊት ትልቁን ዓላማ ለዓለም ያለውን ተገንዘብ (ማለትም፣ ባርኮት ወይም ፍርድ፣ መዝ. 58:11፤ 65:8) ይኸውም ሰዎች ሁሉ እሱን እንዲያውቁት ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)።

ቁጥር 9 በርግጥ ግነታዊ ነው እናም በእስራኤል ባሉት ላይ ምን እንደሚሆን ያንጸባርቃል፣ ነገር ግን እንደ ሌሎቹ በርካታ ቁጥሮች፣ ትልቁን እውነት ያስቀምጣል (መዝ. 46:10)።

**64፡10** ይህ ቁጥር የተለየ የመዝጊያ ዓረፍተ ነገር ነው። ዘወትር የመዝጊያው ዓረፍተ ነገር በመዝሙር ላይ

1. ምስጋና ለእግዚአብሔር ነው

2. የምስጋና መሥዋዕት።

◘ **“ጻድቅ ሰው”** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 1፡5 ላይ።

◘ **“ደስ ይለዋል”** የቃላት መቀያየር ሊኖር ይችላል

1. ይሰማል፣ ቁ. 1 – ሄמ – (ቢ.ዲ.ቢ. 1033)
2. ደስ ይለዋል፣ ቁ. 10 – חמש (ቢ.ዲ.ቢ. 970)

ይህም የአካታች (ኢንክሉሲአ) መልክ ይሆናል።

◘ **“መታመኛ”** መዝሙር 5፡11 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

◘ **“ይከብራል”** አየተመት ግሦቹን የሚመለከታቸው “ደስ ይለዋል” በሚል ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 970፣ ኬቢ. 1333) እና “ይከብራል” (ቢ.ዲ.ቢ. 237፣ ኬቢ. 248) ያልተጠናቀቁት በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ እንደሚውሉ። አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች የሚመለከቷቸው በሂደት ላይ እንዳሉ ዓረፍተ ነገሮች ነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በዚህ መዝሙር ላይ ለምን ይሄን ያህል ግለሰባዊ ሰቆቃዎች ሊኖሩ ቻሉ?
2. በገዛ ራስህ ቃላት የቁጥር 6ን የመጨረሻ ስንኝ አብራራ።
3. የ “የተገላቢጦሽን” ጽሑፋዊ ጽንሰ-ሐሳብ አብራራ፣ ይኸውም በብኪ እጅግ የተለመደ የሆነ።
4. ቁጥር 9 የሚያመለክተው እስራኤልን ነው ወይስ ዓለምን?

# መዝሙር 65
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የአምላክ የተትረፈረፈ ሞገስ ለምድና ለሰው<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር። | ምስጋና ለአምላክ ስለ ማዳኑና ስለ ስጦታው | ስለ መልካም አዝመራ እግዚአብሔርን ማመስገን | ውዳሴና ምስጋና | የምስጋና መዝሙር |
| 65:1-4 | 65:1-3 | 65:1-4 | 65:1-4 | 65:1-2ሀ |
| | | | | 65:2ለ-3 |
| | 65:4 | | | 65:4 |
| 65:5-8 | 65:5-8 | 65:5-8 | 65:5-8 | 65:5 |
| | | | | 65:6-7ለ |
| | | | | 65:7ሐ-8 |
| 65:9-13 | 65:9-10 | 65:9-13 | 65:9-13 | 65:9ሀ-መ |
| | | | | 65:9ሦ-13 |
| | 65:11-13 | | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር ሁለንተናዊ ግፊት አለው (ዝከ. ቁ. 2፣5፣8) ስለ ፍጥረት አምላክ ከማመልከቱ የተነሣ።

ለ. የእግዚአብሔር ዓላማ ለምድር በረከትና ጤንነት ነው (ዘፍጥረት 1-2፤ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 28-30)፣ የሰው ልጅ ግን ዐመጸ (ዘፍጥረት 3) እና ዓመጻውን ቀጠለ (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27)፣ይኸውም በሁለቱም በመንፈሳዊም ሆነ በሥጋዊው መዘዝ ያለው (ሮሜ. 8፡18-25)።

ሐ. መዝሙሩ ዋነኛውን የበረከት ዓላማ ያስታውሰናል (ዝከ. ቁ. 9-13)፣ እሱም አሁን የአዲሱ የመታደስ ዘመን ተስፋ የሆነ (ኢዩኤል 4፡18፤ አሞጽ 9፡13)። ይህ አዲስ ዘመን ሞላውን ዓለም ይባርካል!

መ. ተተኳሪዎች አለመኖራቸውን ተገንዘብ (አንድ ተጓዳኝ ብቻ፣ ቁ. 4)። ይህ መዝሙር የጸሎት ጥያቄ አይደለም ነገር ግን የእግዚአብሔር ድርጊቶች ማስረገጫ እንጂ፣ በጸጋውና በደጋፊነቱ። እሱ አማኞችን ከዓለም ሁሉ ይፈልጋል!

**መዝሙር ፡ 65፡1-4**

[1]አቤቱ፥ በጽዮን ለአንተ ምስጋና ይገባል፥
ለአንተም ጸሎት ይቀርባል።
[2]ሥጋ ሁሉ ጸሎትን ወደምትሰማ
ወደ አንተ ይመጣል።
[3]የዓመፃ ነገር በረታብን
ኃጢአታችንንስ አንተ ይቅር ትላለህ።
[4]አንተ የመረጥኸው
በአደባባዮችህም ለማደር
የተቀበልኸው ምስጉን ነው
ከቤትህ በረከት እንጠግባለን።

**65፡1** አንድ *ግሥ* ብቻ ነው ያለው (ቢዲቢ 1022፤ ኬቢ 1532፣ *ፖል ያልተጠናቀቀ*) ቁ. 1 ላይ። እሱም ከብዙ ዓይነቶች ጋር የሚያያዝ ይመስላል።
1. በፊትህ ዝም ይላሉ (መዝ. 62፡1፤5)
2. ምስጋና በጽዮን
3. ስዕለት ተፈጸመ (የምስጋና መሥዋዕት)

ይህ በግልጽ የአምልኮ መቼት ነው፣ በመቅደስ (ዝከ. ቁ. 4)።

ከታች ተመልከት ቁ. 1 እና ቁ. 2 አንድ ዓይነት ሊሆኑ ይችላሉ። እንደዚያ ከሆነ፣ እግዚአብሔርን ማመስገንና ስዕለትን መፈጸም የሰው ልጅ ኃላፊነት ነው።

◘

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በፊትህ ዝም ይላሉ"** |
| **አኪጀት** | **"በምስጋና አንተን ይጠብቃሉ"** |
| **አየተመት** | **"ምስጋና ላንተ ይገባል"** |
| **አኢመቅ** | **"ምስጋና በእውነት ላንተ ነው"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ምስጋና ላንተ ይገባል"** |
| **የተእመቅ** | **"አንተን ማመስገን ይገባል"** |
| **LXX** | **"ላንተ ዝማሬ ይገባል"** |

ኤምቲ "ዝምታ" የሚል አለው (ቢዲቢ 189፣ דּוּמִיָּה ) ነገር ግን የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ተመሳሳይ ተባባቢዎችን ይሰጣል፣ በተለያዩ አናባቢዎች (ማለትም፣ "ይገባል") በ"ለ" ደረጃ (መጠነኛ ጥርጣሬ)። አንዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች በዚህ ይስማማሉ። ይኸም LXX፣ ፔሺታ፣ እና ቫልጌት ትርጉሞች ይከተሉታል። ሆኖም፣ "ዝምታ" ሊገልጽ የሚችለው የኃጢአተኝነትን ስሜት ነው፣ በእግዚአብሔር ፊት (መዝ. 39፡2) እና በፊቱ ተስፋ አድርጎ ደጅ የሚጸናን (መዝ. 62፡1)።

◘ **"ጽዮን"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 2፡6፤ 9፡11፤ 20፡2 ላይ።

**65፡2** የፍጥረት አምላክ ባሕርዩ
1. እንደሚሰማ ነው – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል* የድርጊት ቦዝ አንቀጽ። ጣዖታት ማየት፣ ማዳመጥ፣ ወይም ማድረግ አይችሉም።
2. *ሥጋ* ሁሉ ወደ እርሱ ይመጣል (ቢዲቢ 142) (ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ)። እዚህጋ አከራካሪ/ተቃርኖ አለ፣ በ... መካከል
   ሀ. *ሥጋ* ሁሉ – ቁ. 2፤5፤8፤ መዝ. 64፡9፤ 66፡1፤4፤8፤ 67፡3-5፤ 86፡9፤ 145፡21፤ ኢሳ. 66፡23፤ ኢዩኤል 2፡28፤ ዘካ. 14፡17
   ለ. የኪዳኑ ሕዝብ – ቁ. 3-4 (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)፤ የብኪ የእግዚአብሔር ሕዝብ የሚያምኑት ሁሉ ሆነዋል (ሮሜ. 2፡28-29፤ ኤፌ. 2፡11-3፡13)

አንዱ ሊደነቅ ይችላል "*ሥጋ ሁሉ*" የሚለው በሚያመለክተው
1. ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መካተት (ማለትም፣ ደኅንነት በይቅርታ)
2. በፍርድ አምላክ መነገር እና ኃላፊነቱን መውሰድ

**65፡3** የፍጥረት አምላክ ይቅር ይላል (ማለትም፣ ይሸፍናል፣ ቢዲቢ 497፣ ኬቢ 493፣ ፔል ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 78፡38፤ 79፡9፤ ኤቢ ይሄንን የሚመለከተው እንዳልተጠናቀቀ ነው፣ እንደ ተተኳሪ ጥቅም ላይ እንደ ዋለ [ገጽ 110])።
1. በደል (ቢዲቢ 730)
2. መተላለፍ (ቢዲቢ 833)

"እኛን" የሚለው መስተጻምር አአመመቅ ላይ የሚያመለክተው እስራኤልን ነው (ዝከ. ቁ. 4)። ይቅርታ ከኪዳን ተስፋ ተፍጻሜት ጋር እንዴት እንደሚዛመድ ተገንዘብ። መታዘዝ ዋነኛ ነገር ነው (ሌዋውያን 26፤ ዘዳ. 11፡13-17፤ ምዕራፍ 28-30)። መታዘዝ ሲቀር ብቸኛው ተስፋ የእግዚአብሔር ምሕረት ነው!

## ልዩ ርዕስ፡ ስለይቅርታ የሚናገሩ ቃላት

መለኮታዊ የሆነ ለሰው ልጆች የሚደረገውን የኃጢአት እና አመፅ የቅረታን ለማሳየት ጥቅም ላይ የዋሉ የእብራይስጥ ቃላት እንደሚከተሉት ናቸው

1. "ይቅርታ፣ " "ምህረት፣ " סלח – BDB 699፣ KB 757፣ ለምሳሌ ፣ ዘፀ 34:9፤ ሌዋ 4:20፣ 26፣ 31፣ 35፤ 5:10፣ 13፣ 16፣ 18፤ 6:7፤ 19:22፤ ዘሑ 14:20፤ 15:25-28፤ 30:5፣ 8፤ 12፤ 1 ነግ 8:30፣ 34፣ 36፣ 39፣ 50፤ መዝ 25:11፤ 103:3፤ ኢሳ 55:7፤ ዳን 9:19፤ አሞፅ 7:2 ( ይህ ቃል ሁል ጊዜ ለሰው ሳይሆን ለእግዚአብሔር ብቻ ነው ጥቅም ላይ የሚውለው)
2. "መጥረግ" " መጋረድ ፣ " נ"א (ይህ ግስ በተለያየ ትርጉም የታወቀ ነው) – BDB 669፣ KB 724፣ ለምሳሌ ፣ ዘፀ 23:21፤ 32:32፤ 34:7፤ ዘኁ 14:18፤ ኢያሱ 24:19፤ መዝ 25:18፤ 32:1፣ 5፤ 85:2፤ 99:8፤ ሚክ 7:18
3. "መሸፈን፣ " "ምትክ፣ " כפר – BDB 497፣ KB 493፣ ለምሳሌ ፣ በዘሌዋዊያ ውስጥ በጣም የታወቀ ነው፤ መዝ 65:3፤ 78:38፤ 79:9፤ኢሳ 6:7፤ 22:14፤ ኤር 18:23፤ Ezek 16:63፤ ዳን 9:24
4. "መጋረድ፣ " "መጥረግ፣ " מחה – BDB 562፣ KB 567፣ ለምሳሌ ፣ ነህ 4:5፤ መዝ 51:1፣ 9፤ ኢሳ 43:25፤ 44:22፤ ኤር 18:23
5. "መፈወስ፣ " רפא – BDB 950፣ KB 1272፣ ለምሳሌ ፣ 2 ዜና 7:14፤ መዝ 41:4፤ 103:3፤ ኢሳ 6:10፤ 57:18፤ ኤር 3:22፤ 17:14፤ 30:17፤ ሆሴ 5:13፤ 14:4
6. "ማለፍ፣ " עבר – BDB 716፣ KB 778፣ ለምሳሌ ፣ ምሳ 19:11፤ አሞ 7:8፤ 8:2፤ ሚክ 7:18
7. "ማጠብ፣ " כבס – BDB 460፣ KB 459፣ ለምሳሌ ፣ መዝ 51:2፣ 7፤ ኤር 2:22፤ 4:14
8. "ማፅዳት፣ " טהר – BDB 372፣ KB 369፣ ለምሳሌ ፣ ሌዋ 16:30፤ መዝ 51:7፤ ምሳ 20:9፤ ህዝ 24:13፤ 36:25
9. "ወደኋላ መጣል፣ " לך – – BDB 1020፣ KB 1527፣ ለምሳሌ ፣ ኢሳ 38:17፤ ሚኪ 7:19
10. "መታጠብ መንፃት፣ " חאט – BDB 306፣ KB 305፣ ለምሳሌ ፣ መዝ 51:7 ( መለኮታዊ በሆነ መንገድ መታጠብን በሚያመለክት መንገድ የተጠቀሰ ይህ ግስ እዝህ ብቻ ነው የሚገኘው)
11. "ፍትን ከርሱ መመለስ סתר – BDB 711፣ KB 771፣ ለምሳሌ ፣ መዝ 51:9
12. "ማስታወስ" (neg)፣ זכר – BDB 269፣ KB 269፣ ለምሳሌ ፣ ኢሳ 43:25
13. "መጠቅጠቅ" (ቃል በቃል "መርገጥ")፣ – כב – BDB 461፣ KB 460፣ ለምሳሌ ፣ ሚክ 7:19

**65፡4 "እንዴት ምስጉን ነው"** መዝሙር 1:1 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

◘ **"የተቀበልከው"** ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ጥሪ ነው አባቶችንና ዝርዮቻቸውን (ማለትም፣ እስራኤል፣ ዘዳ. 4:37፤ መዝ. 33:12)። አስደናቂው ነገር ባጠቃላይ ምርጫው ከእስራኤል ብቻ ወደ ሰዎች ሁሉ መረማመዱ ነው (ዝኪ. ቁ. 2፣5፣8)። ይህም ዘፍ. 3:15ን ያመለክታል፣ ይኸውም የድል መለኮታዊ ተስፋ የሆነ፣ ለሚያምኑ ሰዎች ሁሉ፣ ለሚያምኑና ለሚቀበሉ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)።

◘ **"ከቤትህ በረከት እንጠግባለን"** ግሥ (ቢ.ዲቢ. 959፣ ኬቢ. 1302፣ ቃል ተጓዳኝ) የሚገልጸው አንዱ ከመልካም ነገር ሙሉ ለሙሉ የተሞላውን ነው (ቢ.ዲቢ. 375)። ይህ ግሥ ሥጋዊ ባርኮትን ብቻ አያመለክትም (ዝኪ. 65፡9-13) ግን ከእግዚአብሔር ጋር የቀረበ ወዳጅነትን እንጂ! እሱ እኛን በራሱ ይሞላናል!

## መዝሙር ፡ 65፡5-8

**5ቤተ መቅደስህ ቅዱስ ነው በጽድቅም ድንቅ ነው።**
**በምድር ዳርቻ ሁሉና በሩቅ ባሕር ውስጥ ላሉ ተስፋቸው የሆንህ፥**
**አምላካችንና መድኃኒታችን ሆይ፥ ስማን።**
**6በጉልበትህ ተራሮችን አጸናሃቸው፥**
**በኃይልም ታጥቀሃል።**
**7የባሕሩን ጥልቀት**
**የሞገድንም ጩኸት**
**ታናውጣለህ።**
**8ከተአምራትህ የተነሣ አሕዛብ ይደነግጣሉ፥ በምድር ዳርቻም የሚኖሩ ይፈራሉ**
**የጥዋትንና የማታን መውጫ ደስ ታሰኛቸዋለህ።**

**65፡5-8** ይህ አንጓ ሁለት የተለያዩ ሁኔታዎችን ይገልጻል።

1. ፍጥረት፣ ቁ. 6፣7፣8ለ
2. ደኅንነት፣ ቁ. 5፣7ሐ፣8ሐ

የፍጥረት ዓላማ በአምላክ አምሳል ለተፈጠረው የሰው ልጅ ስፍራ እንዲሆን ነበር (ዘፍ. 1፡26-27) ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ለማድረግ (ዘፍ. 3፡ 8)። ከዘፍጥረት 3 በኋላ፣ ይህ ሐሳብ የእግዚአብሔር የማዳንና የመታደስ ግብ ሆነ፣ ለሁሉም የአዳምና ሔዋን ልጆች (ዘፍ. 3፡15)።

ሁለቱም "ተራራ" ቁጥር 6 ላይ እና "ሞገድ" ቁጥር 7 ላይ ሕዝቦችን የሚጠቅስ ነው፣ ፍጥረትን ሳይሆን (ኤር. 51፡25)። እንደዚያ ከሆነ፣ ይህ ትይዩ ነው ከዘዳ. 32፡8 ጋር።

ቁጥር 5 እግዚአብሔር መልስ እንደሰጠ ይጠቅሳል፣ ነገር ግን ምንም የተለየ ጸሎት አልተጠቀሰም። እሱም የማዳን ጸሎት እንደሆነ ግልጽ ነው ከ

1. ከግልና ከብሔራዊ ኃጢአት
2. ከብሔራዊ ጠላቶች (ማለትም፣ ግብፅ፣ ሶርያ፣ ባቢሎን፣ መዝ. 2፡1-3)
3. ምናልባትም የፍጥረት ሁከት ራሱ (ቁ. 7)

**65:5**
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**
**አየተመት** **"አስደናቂ ድርጊቶች"**
**አእቅ** **"አስደናቂ ነገሮች"**
**አኢመቅ** **"ድንቆች"**

ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 431 በኒፋል) ለእግዚአብሔር ድርጊቶች ነው ጥቅም ላይ የዋለው።
1. እስራኤላውያንን ከግብፅ የማውጣት ድርጊት – ዘጸ. 34:10፤ ዘዳ. 10:21፤ መዝ. 66:3፣5፤ 106:22
2. ያህዌ ራሱ – መዝ. 47:2፤ 68:35፤ 76:7፤ 145:4-7
3. የያህዌ ስም – ዘዳ. 28:58፤ መዝ. 99:3፤ 111:9፤ ሚል. 1:14
4. በጣም አጠቃላይ (ማለትም፣ ተውሳከ ግሣዊ) – መዝ. 66:5፤ 139:14

◘ **"በምድር ዳርቻ ሁሉና በሩቅ ባሕር ውስጥ ላሉ ተስፋቸው የሆንህ፣"** እንዴት ያለው ብርቱ፣ አካታች መግለጫ ነው። እሱም የ "አሀዳዊነት" ሎጂካዊ ዘርፍ (መስፋፊያ) ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 2፡7 ላይ)።

◘
**አአመመቅ፣ አእቅ፣**
**ጀፒኤስአኤ** **"መታመኛ"**
**አኪጀት** **"መተማመኛ"**
**አየተመት፣ አኢመቅ** **"ተስፋ"**

ይህ ስም (ቢ.ዲ.ቢ. 105) በቢ.ዲ.ቢ. የተመለከተው "የመተማመኛ ዓላማ" በሚል ነው (ኢዮብ 8:14፤ መዝ. 40:4፤ 71:5፤ ኤር. 3:37)፣ ይኸውም በዚህ ቁጥር ያህዌ ነው፣ የአሕዛብ የሐሰት ጣዖታት ሳይሆኑ (ዝከ. "የሕዝቦች ጩኸት፣" ቁ. 7ሐ፣ መዝሙር 2)።

◘ **"የምድር ዳርቻ"** እንዴት ያለው ተደጋጋሚ ሐረግ ነው፣ በተለይም መዝሙራትና ኢሳይያስ ላይ። ይህ ሐረግ የሚቀርበው በሁለት መስተጻምሮች ነው፣ "ወደ" ... "ከ።"

1. "ወደ" — ያህዌ ሰው እና ድርጊቶች
   ሀ. መመለስ – ዘዳ. 30:4
   ለ. ፈራጅ – 1 Sam.2:10 (cf. Ps. 82:8፤ 96:13፤ 98:9)
   ሐ. ስያሜና ምስጋና – መዝ. 48:10 (cf. ኢሳ. 42:10፤ ሚል. 1:11)
   መ. ይገዛል – መዝ. 59:13
   ሠ. ተስፋ – መዝ. 65:6
   ረ. ፍርሃት/ድንጋጤ – መዝ. 67:7 (መዝ. 33:8)
   ሰ. ልዑል – መዝ. 83:18፤ 97:9
   ሸ. ደኅንነት – መዝ. 98:3 (ወደ ጌታ መመለስ፣ መዝ. 22:27)፤ ኢሳ. 49:6፤ 52:10፤ 62:11
   ቀ. ፈጣሪ – ኢሳ. 40:28
   በ. የሚቤዥ – ኢሳ. 48:20
   ተ. የመሲሑ አገዛዝ – መዝ. 2:7፤ ሚክያስ 5:4
2. "ከ" — ወደ እርሱ ከመጣው ዓለም
   ሀ. የምድር ዳርቻ ያስታውሳል ወደ ጌታም ይመለሳል — መዝ. 22፡27
   ለ. እስከ ምድር ዳርቻ ዝማሬ እናዳምጣለን፣ "ክብር ለጻድቁ" — ኢሳ. 24፡16
   ሐ. የምድር ዳርቻ ሁሉ ይድናል – ኢሳ. 45:22-23
   መ. ምድር ሁሉ ወደ እርሱ ይመጣል፣ በጽዮን – ኢሳ. 2:2-5፤ 60:3፤ 66:18፣23፤ ኤር. 16:19

**65፡7** ይህ ቁጥር የሚያመለክተው
1. ፍጥረትን (ማለትም፣ በሁከት የተሸነፈ)
2. ከአመንዝራነት (ጣዖት አምልኮ) ጋር ግጭት (መዝሙር 2፤ ኢሳ. 17፡12)

**65፡8 "በፍርሃት ይቆማሉ"** ተመሳሳይ ሥር እንደ ቁጥር 5፣ "አስፈሪ ድርጊቶች።"

◘ ***"ተአምራትህ"*** ይህ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን የማዳን ድርጊት ነው፣ ሕዝቡን (ማለትም፣ የአባቶች መጠራት እና መጠበቅ፤ ዘጸአት እና የምድረ-በዳ እንክርት፣ ድል ማድረግ፣ ወዘተ...)።

◘ የቁጥር 8 የመጨረሻው ሐረግ ሊያመለክት የሚችለው
1. ፍጥረት (ማለትም፣ ማታ እና ጠዋት)
2. የከዋክብት ብልጭልጭታ (ኤቢ)
3. ምስራቅ እና ምዕራብ እንደ አካታች መልክዓ ምድራዊ ዘይቤአዊ አገላለጽ (አእት መጽሐፍ ቅዱስ)
4. የቀን እና የማታ ክብር (ቲንዳሌ ሐተታ)

**መዝሙር ፡ 65፡9-13**

[9]ምድርን ጐበኘሃት አጠጣሃትም፥
ብልጥግናዋንም እጅግ አበዛህ
የእግዚአብሔርን ወንዝ ውኃን የተመላ ነው
ምግባቸውን አዘጋጀህ እንዲሁ ታሰናዳለህና።
[10]ትልምዋን ታረካለህ፥
ቦይዋንም ታስተካክላለህ
በነጠብጣብ ታለሰልሳታለህ፥
ቡቃያዋንም ትባርካለህ።
[11]በቸርነትህ ዓመትን ታቀዳጃለህ፥
ምድረ በዳውም ስብን ይጠግባል።
[12]የምድረ በዳ ተራሮች ይረካሉ፥
ኮረብቶችም በደስታ ይታጠቃሉ።
[13]ማሰማርያዎች መንጎችን ለበሱ፥
ሸለቆችም በእህል ተሸፈኑ
በደስታ ይጮኻሉ ይዘምራሉም።

**65፡9-13** ይህ *ሥጋዊ* በረከት ነው፣ ኪዳናዊ ታዛዥነት የሚያመጣው (ሌዋውያን 26፤ ዘዳ. 11፡13-17፤ ምዕራፍ 28)። በረከት የያህዌ መንገድ ነው፣ ዓለም ወደ እርሱ እንዲመጣ ለማድረግ፣

1. ፍቅር
2. ክብካቤ
3. ደጋፊነቱን

ለእስራኤል በማሳየት። እሱ እስራኤልን መረጠ ሁሉንም ለመምረጥ! እስራኤል ግን ታዛዥ አልሆነም (ሕዝ. 36፡22-23)።

የ "የአንተ"ን ቁጥር ተገንዘብ፣ በእንግሊዝኛ ትርጉሞች፣ ቁ. 9-11 (ማለትም፣ ዘጠኝ)። ፍጥረት ለፈጣሪው በበረከት ምላሽ ይሰጣል!

**65፡9 "ምድርን ጎበኘሃት"** ይህ ፈሊጥ ነው፣ ለያህዌ አካላዊ መገኘት። እሱ ዘወትር በምድር ላይ ነው፣ በሚል መልኩ። ይህ ምስያ የሚናገረው ግን ለልዩ ምጽአቱ ነው፣ አንድም ለፍርድ አልያም ለበረከት። እዚህ የግብርና ምርት በረከት ነው፣ በበረከት ዝናብ የተገኘ።

▣ **"ውኃን የተሞላ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 1003፣ ኬቢ 1448፣ *ፖለል ያልተጠናቀቀ*) ሦስት ጊዜ ይከሰታል፣ እዚህ፣ ዘወትርም "ተባረክ፣" በሚል የሚተረጎም እና ኢዩኤል 2፡24፤ 3፡13፣ እሱም "ውኃን የተሞላ" በሚል የተተረጎመ።

▣ **"የእግዚአብሔር ወንዝ"** ይህ ሐረግ የሚለው

1. የሞላ ውኃ ምስያ
2. ከሰማይ የሚወርድ ዝናብ (መዝ. 78:23፤ ሚል. 3:10)
3. የፍጻሜ ዘመን ጠቃሽ፣ ከእግዚአብሔር ዙፋን ከሚፈስሰው ወንዝ (መዝ. 46:4፤ ሕዝ. 47:1፤ ራዕ. 22:1)

**65:11**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | ***"መንገዶችህ በስብ ተሞልተዋል"*** |
| **አየተመት** | ***"ተሽከርካሪ ሠረገሎችህ በበረከት የተሞሉ ናቸው"*** |
| **አእቅ** | ***"በምትሄድበት ሁሉ በረከት ይገኛል"*** |
| **አኢመቅ** | ***"ብልጥግና ከተሽከርካሪህ ይንጠባጠባል"*** |
| **ጀፒኤስአኤ** | ***"ስብ በመንገድህ ላይ ይንጠባጠባል"*** |

ኤምቲ "እናም የሠረገሎችህ ተሽከርካሪዎች ስብ ያንጠባጥባሉ" የሚል አለው። ይህ የያህዌ ምስያ ነው፣ በሙብረቅማ ደመና መንኮራኩር ሲጓዝ፣ ዝናብ ለማምጣት (መዝ. 18:7-15)። ይህ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ)፣ ወይም በተለይ የከነአን፣ ምናብ ነው፣ የበአል፣ የማዕበል ጣዖት (ማለትም፣ በረከት)።

**65፡12-13** የተባረከ *ሥጋዊ* ስፍራ (ማለትም፣ ማሰማሪያ፣ ኮረብቶች፣ ሣርማ መስክ፣ ሸለቆዎች) ሰውኛ ዘይቤ ሆነዋል፣ በደስታም ይጮኻሉ (ቢዲቢ 929፣ ኬቢ 1206፣ *ሂዝፓል ያልተጠናቀቀ*) ይዘምራሉም (ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*)። ይህ ሕይወት የሌላቸው ነገሮች ምስጋና የኢየሱስን ቃል ያስታውሰኛል፣ ስለ ድንጋዮቹ፣ ሉቃስ 19፡40። አንድ ቀን ፍጥረት ሁሉ (ሕይወት ያለው እና ሕይወት የሌለው) በደስታ በፈጣሪው ፊት ይጮኻል (መዝ. 103:20-22፤ 145:10፤ ሮሜ. 8:18-25)!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ለመዝሙረኛው ስዕለት ቁጥር 1 ላይ ስላለው ነገር የተሻለው ግምት ምንድነው?
2. ፍጥረትና "የዓለም ዳርቻ" እንዴት ይያያዛል?
3. የቁጥር 3ን ሥነ-መለኮታዊ ጠቀሜታ አብራራ።
4. "ተራሮች" እና "የሕዝብ ሁከት" እንዴት ትይዩ ይሆናል?
5. ቁጥር 9-13 የሚገልጸው ዓመታዊ ሁነትን ነው ወይስ የፍጻሜ ዘመን ሁነት?
6. ቁጥር 2፣ 5፣ እና 8ን ከቁጥር 4 ጋር እንዴት ማመዛዘን ይቻላል?

# መዝሙር 66
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ምስጋና ለእግዚአብሔር ስለ ታላቅ ሥራው እና ለጸሎት ምላሽ በመስጠቱ ኤምቲ መግቢያ ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር | ምስጋና ለእግዚአብሔር ስለ ታላቅ ሥራው | የውዳሴና የምስጋና አምልኮ | የውዳሴ ዝማሬና ምስጋና | የአንድነት የምስጋና ጸሎት |
| 66:1-4 | 66:1-4 | 66:1-4 | 66:1-4 | 66:1-3ሀ |
| | | | | 66:3ለ-4 |
| 66:5-7 | 66:5-7 | 66:5-7 | 66:5-9 | 66:5-6ለ |
| | | | | 66:6ሐ-7 |
| 66:8-15 | 66:8-12 | 66:8-12 | | 66:8-9 |
| | | | 66:10-12 | 66:10-12 |
| | 66:13-15 | 66:13-15 | 66:13-15 | 66:13-14 |
| | | | | 66:15 |
| 66:16-20 | 66:16-19 | 66:16-19 | 66:16-19 | 66:16-19 |
| | 66:20 | 66:20 | 66:20 | 66:20 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ዴሪክ ኪድነር፣ በቲንዳሌ የብሉይ ኪዳን ሐተታ ተከታታይ ላይ (ገጽ 251) ለዚህ መዝሙር ርዕስ ሰጥቶታል፣ "የሁሉም አምላክ... የብዙዎች... የአንዱ" የሚል። ይህም የዚህን መዝሙር ዋነኛ ሐሳብ ለመያዝ አስደናቂ መንገድ ይመስላል። እሱም በሁለንተናዊ አጽንዖት ይጀምራል፣ እናም ወደ እስራኤል ምስጋና ያመራል በመጨረሻም ወደ አንድ አምላኪ ከፍታ ይመጣል።

ለ. ይህ መዝሙር እንደ ተጎራባቾቹ እጅግ ተመሳሳይ ነው፣ መዝሙር 65 እና 67። እነርሱ ሁሉ የሚናገሩት ስለ እግዚአብሔር ሁለንተናዊ ፍቅር ነው፣ ሰዎችን ሁሉ። በዚህ መንገድ እነርሱ እጅግ ተመሳሳይ ናቸው፣ ከነቢዩ ኢሳይያስ እና ዮናስ ጋር።

ሐ. የዚህ መዝሙር ታሪካዊ መቼት ርግጠኝነት የለውም። ርግጥ ነው የዓረብኛው ትርጉም፣ "የዳዊት መዝሙር" ይላል፣ ነገር ግን የሚመስለው ይህ መዝሙር በተሻለ የሚገጥመው ከሕዝቅያስ ሕይወት ጋር ነው። ብሔራዊ ጥፋትና ግለሰባዊ ውድቀት አለ። የሚመስለውም የሶርያ ወረራ፣ በሰናክሬ ሥር ኢየሩሳሌም መከበቧና የሕዝቅያስ ሕመም፣ ወደ ሞት አምርቶት ነበር፣ ወደ እግዚአብሔር በጸሎት ሳይቀርብ፣ የሚለው በተሻለ ለዚህ መዝሙር ይሰማማል።

መ. ስምንቱ ተተኳሪዎች በዚህ መዝሙር ላይ ወደ እግዚአብሔር ጸሎት አይደሉም፣ ማሳሰቢያዎች እንጂ
1. በምድር ላይ ላሉ ሰዎች ሁሉ (ዝከ. ቁ. 1፣4፣8)
2. እግዚአብሔርን ለሚፈሩ/ለሚደነቁ/ለሚያከብሩ ሁሉ (ዝከ. ቁ. 16)

***መዝሙር ፡ 66:1-4***

**[1]በምድር ያላችሁ ሁሉ ለእግዚአብሔር እልል በሉ፥**
**[2]ለስሙም ዘምሩ፥**
**ለምስጋናውም ክብርን ስጡ።**
**[3]እግዚአብሔርን እንዲህ በሉት። ሥራህ ግሩም ነው**
**ኃይልህ ብዙ ሲሆን ጠላቶች ዋሹብህ።**
**[4]በምድር ያሉ ሁሉ ለአንተ ይሰግዳሉ፥**
**ለአንተም ይዘምራሉ፥**
**ለስምህም ይዘምራሉ። ሴላህ።**

**66:1 "እልልታ"** ይህ ኒፋል ተተኳሪ የብዙ ቁጥር ነው፣ እናም ቁጥር 1 ከመዝሙር 100 ጋር ተመሳሳይ ነው፣ እኔንም የሚያስታውሰኝ የተዋበውን ኅብረ-ዝማሬ ነው የራዕ. 7:9ን። የብዙ ቁጥሩ የሚናገረው ምድር ሁሉ ለእግዚአብሔር በደስታ እልል እንደሚል መሆኑን ተገንዘብ (ዝከ. ቁ. 1፤4፤ 8፤ መዝ. 65:2፤5፤8፤ 67:17)።

ይህ መዝሙር የእግዚአብሔርን ሁለንተናዊ ስም፣ *ኤሎሂምን* እንደሚያካትት ተገንዘብ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:1 ላይ)፣ የእግዚአብሔርን የኪዳን ስም፣ ያህዌን ሳይሆን። ምድር ሁሉ ነው ምላሽ የሚሰጠው (መዝሙር 67)፤ የእስራኤል ምስጋና በቂ አልሆነም (መዝ. 103:19-22፤ 145:21፤ 150:6)። ይህ እውነት ከሆነ አንድ አምላክ ብቻ አለ፣ እሱም ሞላውን ዓለም የፈጠረና ሰውንም በአምሳሉ የሥራ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት መዝ. 2:7 ላይ)፣ ከዚያም እውነትነቱ ግልጽ ነው፣ ሰዎች ሁሉ እሱን ወደ ማወቅ እንዲመጡ መፈለጉ። እስራኤል ማለት የመንግሥት ካህናት እንዲሆን ብቻ ነው፣ ዓለምን ወደ እግዚአብሔር ለማምጣት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ፣ መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)።

**66:2 "ለስሙ ክብር ዘምሩ"** በአምልኮ ጊዜ የመዘመር ሐሳብ ወይም ጽንሰ-ሐሳብ የተወሰደው ከእንደዚህ ዓይነቶቹ መዝሙር ላይ ነው። አስደናቂ የሚሆነው ኤፌ. 5:19 ላይ፣ እዚያም በመንፈስ ቅዱስ ስለ መሞላት የሚናገረው፣ ማለትም ከቀጣዮቹ አምስት ቦዝ አንቀጾች ሦስቱ ስለ ዜማ የሚናገሩ ናቸው። ምስጋና ተገቢ የሆነ ድርጊት ነው፣ አምላካችንን በማምለክ ላይ።

"ስም" የሚለው ቃል በዕብራይስጥ የአንዱን ባሕርይ ማንጸባረቂያ መንገድ ነው። እሱም ዘወርዋራ መንገድ ነው የዕብራይስጥን ፍርሃት ለመግለጫ የራሱን የእግዚአብሔርን ስም ለማንሣት፣ በዚያም ምክንያት ነው የስሙ ጽንሰ-ሐሳብ በየጊዜው የሚቀያየረው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5:11-12 ላይ)።

ታማኝ ተከታዮች የያህዌን ባሕርይና ድርጊት ያመሰግናሉ (መዝ. 29:2፤ 79:9፣ 96:8)። "ስሙ" ራሱን ያህዌን ይወክላል (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5:11-12 ላይ)።

"ክብር" ለሚለው ቃል ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 19:1 ላይ።

**66:3 "ለእግዚአብሔር በሉ"** ይህ አራተኛው ተተኳሪ ነው የቁጥር 1-3 ለሰዎች ሁሉ የታዘዘ።

1. ለእግዚአብሔር በደስታ እልል በሉ – ቢዲቢ 929፣ ኬቢ 1206፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 47:2፤ 81:2፤ 98:4፤6 (ተጓዳኝ መዝ. 95:1፤2 ላይ)
2. ለስሙ ክብር ዘምሩ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ *ፔል ተተኳሪ*፣ መዝ. 9:11፤ 30:4፤ 47:6-7 [አምስት]፤ 105:2፤ 135:3 (ተጓዳኝ መዝ. 18:49፤ 27:6፤ 59:16፤ 71:22፤ 75:9፤ 101:1፤ 104:33፤ 146:1 ላይ)
3. ለምስጋናውም ክብርን ስጡ – ቢዲቢ 962፣ ኬቢ 1321፣ *ቃል ተተኳሪ* ("አስቀምጡ፣" "አድርጉ፣" ወይም "አኑሩ")፣ ኢሳ. 42:12
4. እግዚአብሔርን በሉት – ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል ተተኳሪ*

▣ ***"ሥራህ እንዴት ግሩም ነው"*** ቃሉ "አስፈሪ" ወይም "የሚያስፈራ" ነው (ቢዲቢ 431፣ *ኒፋል አንቀጽ*፣ መዝ. 45:4፤ 65:5)። አንዳንድ ተርጓሚዎች፣ እንደ ኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ ያሉት፣ ይህን የሚተረጉሙት፣ "ከፍታህ እንዴት አስፈሪ ነው" በሚል ነው፣ ነገር ግን የሚመስለው በቁጥር 5 ምክንያት ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ እየተናገርን አይደለም፣ ስለ እግዚአብሔር ድርጊት እንጂ (ዘጸ. 34:10፤ ዘዳ. 10:21፤ መዝ. 65:5፤ 139:14፤ 145:6)። እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ሠርቷል (ዘጸአት 5-7 ላይ)። ድርጊቶቹ የማዳን ድርጊቶችና የዓላማው መገለጥ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)።

▣ ***"ኃይልህ ብዙ ሲሆን ጠላቶች ዋሹብህ"*** ይህ በዕብራይስጥ እጅግ አስቸጋሪ ዓረፍተ ነገር ነው፣ ለመተርጎም። ርግጥ ነው የእግዚአብሔር ኃይል እምቢተኛ ጠላቶቹን ሳይቀር እንዲያመሰግኑ ያደርጋል (መዝ. 18:44)። ዕብራይስጡ ማለት የሚሻው "የማስመሰል መታዘዝ" ነው (ቢዲቢ 471፣ ኬቢ 469፣ ፔል ያልተጠናቀቀ)። ሴፕቱዋጂንት እንዲያውም የሚተረጉመው፣ "ውሸት" በሚል ነው። የዕብራይስጡ ቃል እያነሰ የሚሄድ ነገር የሚል ፍች አለው፣ ኩራት እየቀነሰ የሚሄድ፣ ወይም አክብሮትን ማጣት (መዝ. 81:15)። ይኸውም የተፈለገው ፍች እዚህጋ ርግጠኛ ያለመሆን ይታይበታል።

**66:4 "በምድር ያሉ ሁሉ ላንተ ይሰግዳሉ"** ይህም ከተመሳሳይ ስንኝ ጋር የሚናገር ይመስላል፣ እንደ ፊሊጵ. 2:9-11፣ ማለትም አንድ ቀን ሁለቱም ወዳጅና ጠላት፣ ሁለቱም ልጅና ጠላት ለያህዌ እውቅና ይሰጣሉ። በዚያን ቀን ሁሉም ለእርሱ ምስጋና ይዘምራሉ (መዝ. 22:27፤ 46:10፤ 65:2፤5፣ 8፤ 67:1-7፤ 86:9፤ ዘካ. 14:16)። ይኸም የፍጻሜ አንድምታዎች አሉት (ሚኪያስ 5:2-5ሀ)።

▣ **"ሴላህ"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 699) ደግሞ በቁጥር 7 እና 15 መጨረሻ ላይ ይከሰታል። መዝ. 3፡2 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት፣ እንዲሁም መግቢያ ለመዝሙር VII።

**መዝሙር ፡ 66፡5-7**

**5ኑ የእግዚአብሔርንም ሥራ እዩ**
**ከሰው ልጆች ይልቅ በምክር ግሩም ነው።**
**6ባሕርን የብስ አደረጋት፥**
**ወንዙንም በእግር ተሻገሩ**
**በዚያ በእርሱ ደስ ይለናል።**
**7በኃይሉ ለዘላለም ይገዛል**
**ዓይኖቹ ወደ አሕዛብ ይመለከታሉ**
**ዓመፀኞች ራሳቸውን ከፍ ከፍ አያድርጉ። ሴላህ።**

**66፡5 "ኑ እዩ"** እነዚህ ሁለቱ ቃል ተተኳሪዎች ከሁለቱ ቃል ተተኳሪዎች ጋር ይገጥማሉ፣ "ኑ እዩ"፣ ቁጥር 16 ላይ ካሉት። እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ የሚሠራ አምላክ ነው፣ እሱም ሰዎችን የመረጠ፣ የእርሱን ድርጊቶች እንዲመዘግቡና እንዲያስረዱ። እግዚአብሔርን ማወቅ እንችላለን፣ ባደረገው፣ ብሎም በተናገረው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተመስጦ መዝ. 19፡7-9 ላይ።

## ልዩ ርዕስ፡ አብርሆት

ባለፉት ጊዜያት እግዚአብሔር ራሱን ለሰው ልጆች ግልፅ በሆነ ሁኔታ ገልጧል፡፡ በሥነ መለኮት ይህ መገለጥ ይባላል፡፡ ይህን ራሱን የገለጠበትን ሁኔታ ለመፃፍና ለማስረዳት የተወሰኑ ሰዎችንም መርጧል፤ ይህም በሥነ-መለኮት እስትንፋስ እግዚአብሔር ይባላል፡፡ ቃሉን የሚያነቡት መረዳት ይችሉ ዘንድ መንፈሱንም ልኰላቸዋል፤ ይህም በሥነ-መለኮት አብርሆት ይባላል፡፡ ችግሩ የሚፈጠረው የእግዚአብሔርን ቃል
ለመረዳት ይቻለን ዘንድ መንፈስ ቅዱስ ይሳተፋል ብለን አስረግጠን ስንናገር ነው፤ ይህ ከሆነ ታዲያ ለምንድነው በቃሉ ላይ ብዙ አይነት አተረጓጐሞችን የምናየው?

የተወሰነው ችግር ያለው በአንባቢው ቅድመመረዳት ወይም ግላዊ ልምምዶች ላይ ነው፡፡ ብዙውን ጊዜ የራሳችንን ሃሳብ ለማስተላለፍ ስንጠቀም ሌላው በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የሚደረገው ጫና ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ በተወሰኑ አቅጣጫዎች በተመረጡ መንገዶች ብቻ እንዲናገር ማድረጋችን ነው፡፡ ምንም እንኳን በእያንዳንዱ ውስጥ የመንፈስ ቅዱስ ተሳትፎ ቢኖርም አብረሆት ከእስትንፋስ እግዚአብሔር ጋር እኩል ሊሆን አይችልም፡፡

ከሁሉም የተሻለው አቀራረብ ግን እያንዳንዱን የጥቅሉን ዝርዝር መተርጐም ሳየሆን የአንቀፁን ማዕከላዊ ሃሳብ ለመረዳት መሞከር ነው፡፡ የመጀመሪያውን ጎሐፊ ማዕከላዊ ሃሳብ ነው፡፡ ርዕሳዊ ሃሳቡን ሊያስተላልፍልን የሚችለው ርዕሳዊ ሃሳቡ ነው መጽሐፉን ወይም ፅሑፉን በንድፈ ደረጃ ማስቀመጥ የመጀመሪያውን ፀሐፊ መነሻ ሃሳብ ለመከተል የሚረዳን ነው፡፡ የትኛውም ተርጓሚ በመንፈስ ቅዱስ ምሪት አልተረገመም፡፡ በመሆኑም የመጽሐፍ ቅዱስ ፀሐፊውን የአተረጓጐም ዘዴ እኛ ስንጠቀምበት አንችልም፡፡ እኛ ግን ፀሐፊዎች በዘመኑ ለነበሩት የመልዕክቱ ተቀባዮች ሊያስተላልፉ የፈለጉትን መረዳት ከዚህም ባሻገር ያንን እውነት ለዘመናችን ማስተላለፍ ግዴታችን ነው፡፡ እንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አሻሚ ወይም ድብቅ ናቸው፡፡ (እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ) በአንዳንድ ጥቅሶችና ርዕሶች ላይ አለመስማማቶች /አለመግባባቶች ይኖራሉ፤ ነገር ግን እኛ ማዕከላዊውን እውነት መግለፅ የተገባን ሲሆን በአንፃሩ ደግሞ የመጀመሪያውን ፀሐፊ ዋና ሃሳብ በጠበቀ መልኩ በግል ለሚሰጡ ትርጉሞች ነፃነትን ልንሰጥ ይገባል፡፡ ተርጓሚዎች መሔድ ያለባቸው ባላቸው የመረዳት መጠን ሲሆን ምንጊዜዋ ከመፅሐፍ ቅዱስት ከመንፈስ ቅዱስ ለሚመጣው ተጨማሪ መረዳት ክፍት መሆን አለባቸው ፡፡ እግዚአብሔርም የሚፈርድብን ባን የመረዳት ደረጃ እና ያንንም መረዳት በምንኖረው ኑሮ ነውና፡፡

▣ **"እሱም በሥራው ግሩም የሆነ"** ከ "ግሩም" ከሚለው ተዛማጅ ቃል የተነሣ (ቢዲቢ 431) እሱም በዘዳ. 4፡34 ጥቅም ላይ በመዋሉ (ቢዲቢ 432) የግብፅን መቅሠፍት ለመግለጽ፣ እንዲሁም ብዙ ጠቃሾች በምድረ በዳ መንከራተት ላይ በዚህ መዝሙር ስላሉ፣ ብዙዎች እነዚህን ድርጊቶች የሚጠቅሱት ለዘጸአት ጊዜ ድርጊቶች ነው።

▣ **"በሰው ልጆች ላይ"** ይህ ጥሬአዊ የሆነ ሐረግ፣ "የአዳም ልጆች፣" የሚያንጸባርቀው እግዚአብሔር ለሰዎች ሁሉ ያለውን ሐሳብ ነው። ዘፍጥረት 3፡15 ለእስራኤል የሆነ ተስፋ አይደለም (እሱም የአብርሃም መጠራት ዘፍጥረት 12 ላይ እስኪሆን ድረስ ያልሆነ)፣ ነገር ግን ለሰዎች ሁሉ እንጂ። መዝሙር 65-67 ይህንን ታላቅ ተስፋ ያንጸባርቃል፣ ኢሳይያስ እና ዮናስ ላይ እንዳለው።

**66፡6 "ባሕርን የብስ አደረጋት"** ይህ ዘጸአትን ነው የሚያመለክተው፣ ዘጸአት 14 (መዝ. 106፡9)፣ ወይም የዮርዳኖስ ወንዝ መከፈል፣ ኢያሱ 3 ላይ (ኢያ. 4፡23)።

**66፡7 "ኃይሉ ለዘላለም ይገዛል"** ይህ ጽንሰ-ሐሳብ እግዚአብሔር በዓለሙ ሁሉ ላይ እንደሚገዛና እንደሚነግሥ የሚያሳይ ነው፣ በእስራኤል ላይ ብቻ ሳይሆን (ማለትም፣ ዘዳ. 32፡8፤መዝ. 47፡7-8፤ ሐዋ 17፤26፤ እና የዋነኞቹ ነቢያት ክፍሎች፣ እግዚአብሔር በአሕዛብ ላይ እንደሚፈርድ የሚያሳዩት)።

▣ **"ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 9፡5 ላይ።

▣ **"ዓይኖቹ ወደ አሕዛብ ይመለከታሉ"** ይህ አሕዛብን በሰውኛ ዘይቤ የሚመለከት ከመሆኑ የተነሣ፣ ብዙዎች የሚያስቡት ይህ የሚያመለክተው የብሔራዊ መላእክትን ጽንሰ-ሐሳብ ነው (የሴፕቱዋጀንት ዘዳ. 32፡8 ትርጉም)። ይህም ደግሞ ሊረጋገጥ የሚችለው በሚያምጹት ሐሳብ ነው፣ ቁጥር 7ሐ ላይ እንዳለው፣ እናም ደግሞ ሊሆን የሚችለው "በሕይወት ጠብቀን" የሚል ነው ቁጥር 9 ላይ፣ ይኸውም ለእስራኤል የወል ጠቃሽ የሆነ። በበይነ-መጽሐፍ ቅዱሳዊ ጊዜ፣ ሰማያዊው ሸንጎ የተዋቀረው በአሕዛብ መላእክት ነው። በአይሁድ ሥነ-ጽሑፍ እነርሱ ከእስራኤል ጋር ጠላትነት ያላቸው ይመስላሉ፣ እናም እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ፍቅር ብቻ ነው፣ ከጥፋት የጠበቃት። ዕዝል XIII እና XIV ተመልከት፣ የአልፍሬድ ኢደርሺም *የመሲሑ ኢየሱስ ሕይወት እና ጊዜ።"*

▣ **"ዓመፀኞች ራሳቸውን ከፍ ከፍ አያድርጉ።"** ኤምቲ ሂፋል ያልተጠናቀቀ አለው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ነገር ግን ማሶረቲካዊ ሊቃውንት የሚሉት በኅዳጉ ላይ የሚነበበው (ቄሬ) እንደ ቃል ያልተጠናቀቀ እሱም በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ እንደዋለ ነው። መልኅቅ መጽሐፍ ቅዱስ ይሄንን ሐረግ የሚተረጉመው "ዓመጸኞች በእርሱ ላይ እንዳይነሡ" በሚል ነው። መደበኛው የተከለሰ ትርጉም ይሄንን ሐረግ የሚተረጉመው፣ "ዓመጸኞች በእርሱ ላይ ሊነሡ አይችሉም" በሚል ነው። ይኸም ከመዝሙር 2 ጋር እጅግ ይመሳሰላል።

**መዝሙር ፡ 66፡8-15**

**8አሕዛብ ሆይ፥ አምላካችንን ባርኩ፥**
**የምስጋናውንም ድምፅ አሰሙ።**
**9ነፍሴን በሕይወት ያኖራታል፥**
**እግሮቼንም ለመናወጥ አልሰጠም።**
**10አቤቱ፥ ፈትነኸናልና፥**
**ብርንም እንደሚያነጥሩት አንጥረኸናልና።**
**11ወደ ወጥመድ አገባኸን፥**
**በጀርባችንም መከራን አኖርህ።**
**12በራሳችን ላይ ሰውን አስረገጥኸን**
**በእሳትና በውኃ መካከል አለፍን፥**
**ወደ ዕረፍትም አወጣኸን።**
**13-14ከሚቃጠል መሥዋዕት ጋር ወደ ቤትህ እገባለሁ**
**በመከራዬ ጊዜ በአፌ የተናገርሁትን**
**ከንፈሮቼም ያሉትን**
**ስእለቴን ለአንተ እፈጽማለሁ።**
**15ከዕጣንና ከወጠጤዎች ጋር**
**ለሚቃጠል መሥዋዕት ፍሪዳን አቀርባለሁ**
**ላሞችንና ፍየሎችን እሠዋልሃለሁ። ሴላህ**

**66፡8-15** ይህ አንጓ የያህዌን መግለጫ ይጠቅሳል፣ ለዐመጸኛው እስራኤል። እሱ ፈርዶባታል፣ ሊያድሳት (ሊመልሳት)። ሰዎች ሁሉ ሊደሰቱ ይገባል፣ ምክንያቱም የያህዌ የመዋጀት ዓላማ በእስራኤል በኩል ለአሕዛብ ሁሉ አሁንም ስለሚሠራ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ)።

**69፡9 "በሕይወት የሚያኖረን"** ይህ ሊሆን የሚችለው (1) የሕዝቅያስ ታሪካዊ ጠቃሽ ነው፣ እሱም በእባጭ ታምሞ በነበረበት ጊዜ፣ እንዲምረው ወደ እግዚአብሔር ሲጸልይ። በኢሳይያስ በኩል ተጨማሪ አስራ አምስት ዓመታት ዕድሜ እንደተሰጠው ሲነገረው፣ (2 ነገሥት 20)። ወይም (2) ለእስራኤል ብሔራዊ ሕይወት የተጠቀሰ በተደጋጋሚ በተወረረችበት ጊዜ፣ ከመካከለኛው ለም መሬት በሚመጡት ጠላቶቿ። ትክክለኛው ጠቃሽ ምንም ይሁን ምን፣ እግዚአብሔር በየጊዜው ለታማኝ ተከታዮች ክብካቤ ማድረጉ የሕይወት ስጦታችን ዋነኛ ነገር ነው። እናም እግዚአብሔር ብቸኛው የሕይወት ባለቤት ነው፣ እርሱም ለሚታመኑት ይሰጣቸዋል (ማለትም፣ መዝ. 65፡5)።

▣ **"እግሮቻችንን ለመናወጥ አልሰጠም"** የዕብራይስጡ ቃል "ማዳለጥ" ("መዋዠቅ፣""መናወጥ፣" ወይም "ማንሸራተት፣" ቢዲቢ 557) ጥቅም ላይ ሊውል የሚችለው

1. አንድን ነገር በእንጨት ላይ መሸከም (ዘኍ. 4:10፣12፤ 13:23)
2. በእስረኛ አንገት ላይ የሚደረግ ዛንጅር (ቀንበር) (ናሆም 1:13)
3. እዚህጋ እሱ የደኅንነት ምስያ ነው። የአንዱ እግሮች በእምነት መንገድ ላይ አይናወጡም (መዝ. 55:22፤ 121:3፤ ግስ መዝ. 15:5፤ 112:6 ላይ)።

ይህ ሐረግ ቀጥተኛ ተቃራኒው ነው "እምነት" ለሚለው የዕብራይስጥ ቃል ፍቺ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 12:1 ላይ)፣ እሱም በዋነኛነት ፍችው "ጸንቶ መቆም" (መዝ. 17:5፤ 38:16፤ 121:3)።

**66፡10 "አቤቱ፥ ፈትነኸናልና፥"** ይህ የመፈተን ጽንሰ-ሐሳብ ነው፣ እሱም ብረትን ከማበጀት ኢንዱስትሪ የተገኘ (ዝከ. ቁ. 10ለ)። እግዚአብሔር ልጆቹን ይፈትናል (ዘፍ. 22:1፤ ማቴ. 4:1)። እሱም ይሄንን የሚያደርገው ሊያጠራን ነው፣ ሊያነጻን፣ እንዲሁም ብርቱዎች ሊያደርገን (ዘካ. 13:9፤ 1 ጴጥ. 1:7)። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 11:4ለ-5 ላይ።

**66፡11 "ወደ ወጥመድ አገባኸን፥"** "አንተ" የሚለው ምን ያህል ጊዜ ቁጥር 10-12 ላይ እንደሚከሰት ተገንዘብ (መዝ. 65፡9-11)። መዝሙረኛው የፍርድ ድርጊቶች ይዘረዝራል፣ ይኸውም የእርሱን ሕዝብ ወደ ንስሐ ስፍራ ለማምጣት፣ እናም ሊባርካቸው (ዝከ. ቁ. 12ሐ)።

“መረብ” (ቢዲቢ 845) የመጣው “ማደን” ከሚለው ሥር ነው (ቢዲቢ 844 II፣ ሕዝ. 13፡21) እናም ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለእንስሳት ወጥመድ ነው (ሕዝ. 12:13፤ 17:20)። ይህ ቃል ዕንባቆም ላይ ጥቅም ላይ ውሏል 1:15-17 የባቢሎንያንን ወታደራዊ መሣርያ ለመግለጽ። ስለዚህ፣ እሱ የእስራኤልን ምድር መወረር የሚጠቅስ ሊሆን ይችላል።

ሌለኛው የዚህ ቃል አጠቃቀም የ “ምሽግ” ሐሳብ ነው (ቢዲቢ 845 II፣ መዝ. 31:3፤ 71:3፤ 91:2፤ 144:2)። ይህም ፈጽሞ የተለየ ፍቺ ያስተላልፋል፣ ወደ ቁጥር 11 በሚተረጎምበት ጊዜ።

▣ **“በጀርባችንም መከራን አኖርህ።”** “ሸክም” የሚለው ቃል (ቢዲቢ 734፣ ኬቢ 558፣ እዚህጋ ብቻ ነው ብኪ ላይ የሚገኘው) ከክብደትም ይልቅ ወደ ኋላ የሚጎትት የሚል ሐሳብ አለው። ቢዲቢ እሱን የሚገልጸው እንደ “ጫና” ወይም “መከራ” ነው። ጀርባ የሰው አካል ጠንካራው ጡንቻ ነው፣ እናም ዘወትር ለሰው ኃይል ዘይቤ ጥቅም ላይ ይውላል (ዘዳ. 33፡11)።

**66፡12 “በራሳችን ላይ ሰውን አስረገጥኸን”** ይህ የሚገልጸው ክፉ ሰዎችን ነው (ማለትም፣ ጣዖት አምላኪ ሕዝቦች) የእግዚአብሔርን ሕዝብ ሲቆጣጠሩ (ኢሳ. 51፡23)።

▣ **“በእሳትና በውኃ መካከል አለፍን፥”** በእሳትና በውኃ መካከል አለፍን እነዚህ ሁለቱ ዘይቤዎች ስለ ብርቱ መከራ የሚናገሩ ናቸው። የኢሳ. 43፡2ን ውብ ዓረፍተ-ነገር ተመልከት፣ ማለትም፣ እግዚአብሔር በመከራችን መካከል እንደማይተወን።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“የበረከት ስፍራ”** |
| **አኪጀት** | **“የብልጽግና ፍጻሜ”** |
| **አየተመት** | **“ወደ ከበረ ስፍራ”** |
| **አእቅ** | **“ወደ ደኅንነት ስፍራ”** |
| **አኢመቅ** | **“በድጋሚ ለማረፍ”** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **“ወደ ብልጽግና”** |
| **የተእመቅ** | **“ወደ በረከት ስፍራ”** |
| **LXX** | **“ለመደገፍ” ወይም “ለመታደስ”** |

ይህ ቃል (ቢዲቢ 924፣ ኬቢ 1201) ለመተርጎም እጅግ አስቸጋሪ ነው። መሠረታዊ ፍችው መሙላት ነው። እሱም መዝ. 23፡5 ላይ ጥቅም ላይ ከዋለው ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው “ጽዋዬም የተትረፈረፈ ነው።” እሱም አንዳንዴ “ሰፊ ስፍራ” በሚል ይተረጎማል (መዝ. 18:19፤ 31:8፤ 118:5)፣ ማለትም የዕረፍት ስፍራ፣ ወይም “ፍሬአማ ስፍራ፣” የተስፋይቱ ምድርን ለማመልከት። እነዚያ ትርጉሞች “ዕረፍት” የሚለውን ቃል የሚያካትቱት እዚህጋ ይሄንን መሠረት ያደርጋሉ፣ በአንድ የዕብራይስጥ ፊደል ለውጥ፣ በዚህ ቃል ላይ (አእት መጽሐፍ ቅዱስን ተመልከት፣ ገጽ 931፣ ቁ. 7)።

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 287) “መሙላት” ለሚለው የ “ለ” ደረጃ ይሰጣል (መጠነኛ ጥርጣሬ) እሱም ሁለት ፍችዎች እንዳለው በመጥቀስ።

1. መትረፍረፍ
2. የዕረፍት ወይም የነጻነት ዓየር

**66፡13-15** ይህ ደራሲው (ዝከ. ቁ. 16ለ፣ ወይም እስራኤል በወል መልኩ) የምስጋና መሥዋዕት እያቀረበና ስዕለቱን እየፈጸመ ነው (ዘኁ. 30፡2፤ ዘዳ. 23፡21-23)።

***መዝሙር* ፡ 66፡16-20**

**16 እግዚአብሔርን የምትፈሩት ሁሉ፥ ኑ፥ ስሙኝ**
**ለነፍሴ ያደረገላትን ልንገራችሁ።**
**17 በአፌ ወደ እርሱ ጮኽሁ፥**
**በአንደበቴም አመሰገንሁት።**
**18 በልቤስ በደልን አይቼ ብሆን**
**ጌታ አይሰማኝም ነበር።**
**19 ስለዚህ እግዚአብሔር ሰማኝ**
**የልመናዬን ድምፅ አደመጠ።**
**20 ጸሎቴን ያልከለከለኝ**
**ምሕረቱንም ከእኔ ያላራቀ**
**እግዚአብሔር ይመስገን።**

**66፡16 “እግዚአብሔርን የምትፈሩት ሁሉ፥ ኑ፥ ስሙኝ”** ይህ ሐረግ የሚጀምረው በሁለት ቃል ተተኳሪዎች ነው (ማስታወሻ ተመልከት ቁ. 5 ላይ)። መጽሐፍ ቅዱስ ዩቨርሳሊዝምን አያስተምርም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ዩቨርሳላዊ የጸጋ ስጦታ ያስተምራል፣ ምላሽ ለሚሰጡት (ዮሐንስ 1:12፤ 3:16፣36፤ 6:40፤ 11:25-26፤ ሮሜ. 10:9-13)። እግዚአብሔር ምላሽ ይሰጣል፣ ምላሽ ለሚሰጡት። ሁኔታውን ግን ተገንዘቡ፣ “እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ።”

▣ **“ለነፍሴ ያደረገላትን ልንገራችሁ።”** ቁጥር 9 የተጠቃለለውን የእስራኤል ሕይወት እንደሚገልጽ፣ ቁጥር 13-15 እና 16-20 ደግሞ የዚህን አንድ አምላኪ ግለሰባዊ ሕይወት ይገልጻል (ማለትም፣ መዝሙረኛው)። እሱም የጸሎት ሕይወቱን ይገልጻል። ዘወትር መዝሙራት የሚጀምሩት በአንድ ግለሰብ ሲሆን፣ የሚጨርሱትም በተጠቃለለ (የወል) ምስጋና ነው፣ ይህ መዝሙር ግን ተቃራኒው ነው።

**66፡17** ምንም ዓይነት የለሆሳስ (ዝምታ) ንባብ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) እንዳልነበረ ሁሉ፣ እንዲሁ ደግሞ የዝምታ ጸሎትም አልነበረም (1 ሳሙ. 1፡13 እይ)።

**66፡18** ዝንባሌ ዋነኛ ነገር ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጸሎት ያልተወሰነ፣ ሆኖም የተወሰነ መዝ. 64፡1። ሰዎች ያልተናዘዙት ኃጢአት ግለሰቡን ያሳውራል፣ ለእግዚአብሔር መገኘትና ፍቅር። ኃጢአትን ማድረግ በጊዜና በዘላለማዊነት ላይ መዘዝ (ውጤት) አለው፣ ለሁለቱም ለአማኝ እና ለማያምን።

**66፡19** ታማኝ ተከታዮች እግአጊዘብሔር እንደሚሰማ ያምናሉ (መዝ. 18፡6) እናም በተገቢው ምላሽ እንደሚሰጥ! ይህ የእምነት ዋስትና ነው፣ የርግጠኝነት ሳይሆን (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዋስትና መዝ. 51፡11ለ)።

**66፡20 "እግዚአብሔር ይመስገን"** ምስጋና (ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ ቃል ተገብሮ አንቀጽ፣ መዝ. 68፡35) የመጣው ከእግዚአብሔር ነው፣ እናም ለእግዚአብሔር። ከእርሱ በቀር ምስጋና የለም። እሱ መባረክ/መመስገን ይገባዋል

1. ለማንነቱ (ዝከ. ቁ. 10-12፤ 2 ቆሮ. 1:3)
2. ላደረገው (ዝከ. ቁ. 1-3)
3. እያደረገ ስላለው
4. ሊያመጣ ስላለው (ዝከ. ቁ. 4፤8)!

◘ **"ቸርነት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ መዝሙር 5፡7 ላይ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙር 66 ከ65 እና 67 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
2. ቁጥር 3 ለመተርጎም ለምን እጅግ አስቸጋሪ ሆነ?
3. ለብሔራዊ መላእክት አንዳች መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃ ይኖር ይሆን (ዳንኤል 10)?
4. እግዚአብሔር ግለሰቦችንና ሕዝቦችን ለምን ይፈትናል?
5. ከጸሎት ጋር የሚያያዙትን ነገሮች ዘርዝር፣ ቁጥር 17-20 ላይ።

# መዝሙር 67
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| አሕዛብ ተነሥተዋል የአምላክን ሥራ ለማመስገን<br>ኤምቲ መግቢያ ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች። ዝማሬ። | የርዳታ ጥሪና ውዳሴ-አምላክ | ስለ መልካም አዝመራ ማመስገን | የምስጋና ዝማሬ | የአዝመራ ዝማሬ |
| 67:1-7 | | | | |
| | 67:1-2 | 67:1-3 | 67:1-2 | 67:1-2 |
| | 67:3-4 | | 67:3 | 67:3 |
| | | 67:4-5 | 67:4 | 67:4 |
| | 67:5-7 | | 67:5 | 67:5 |
| | | 67:6-7 | 67:6-7 | 67:6-7 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር ልክ እንደ መዝሙር 65 እና መዝሙር 66፣ ሁለንተናዊ ይዘት አለው (ዝኪ. ቁ. 2፤3፤4፤5፤7፣ በተለይም ቁ. 2)። የያህዌ ግብ
1. ዓለም እሱን እንዲያውቀው (ቁ. 2ሀ)
2. ዓለም እንዲድን (ቁ. 2ለ)
   እሱም ራሱ እንዲታወቅ አድርገል
1. በፍጥረት ድርጊት በኩል
2. በምርጫ ድርጊት በኩል (ማለትም፣ አብርሃምና ዘሩ)
3. በመዋጀት ድርጊት በኩል (ማለትም፣ በተለይ ዘጸአት፣ የምድረ-በዳ መንከራተት፣ እና ከግዞት መመለስ)
4. እነዚህ ድርጊቶች ተመዝግበዋል፣ ሁሉም ከቅዱስ ቃሉ እንዲያነባቸው
5. ቀጣይ ድርጊቶች በተስፋና በትንቢት፣ በመሲሑ በኩል

ለ. መዝሙሩ ባሕርይ ያደረገው ተጽዕኗዊዎችን በመጠቀም ነው።
1. የእግዚአብሔር ድርጊቶች
   ሀ. እግዚአብሔር ይክበር፣ ቁ. 1 – ቢ.ዲቢ. 138፣ ኬቢ. 159፣ ፔል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   ለ. እግዚአብሔር ይባረክ፣ ቁ. 1 – ቢ.ዲቢ. 138፣ ኬቢ. 159፣ ፔል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   ሐ. እግዚአብሔር ፊቱን በአንተ ላይ ያብራ፣ ቁ. 1 – ቢ.ዲቢ. 21፣ ኬቢ. 24፣ ሂፊል ተጽዕኗዊ
   መ. እግዚአብሔር ይባረክ፣ ቁ. 7 – ቢ.ዲቢ. እንደ ለ ተመሳሳይ
2. የሰዎች ምላሽ
   ሀ-ለ. ሰዎች ያመሰግናሉ (ሁለቴ)፣ ቁ. 3 – ቢ.ዲቢ. 392፣ ኬቢ. 389፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   ሐ. አሕዛብ ደስ ይላቸዋል፣ ቁ. 4 – ቢ.ዲቢ. 970፣ ኬቢ. 1333፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   መ. አሕዛብ በደስታ ይዘምራሉ፣ ቁ. 4 – ቢ.ዲቢ. 943፣ ኬቢ. 1247፣ ፔል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

ሥ-ረ. የቁጥር 3 ድጋሚ (ማለትም፣ ሀ-ለ)

ሐ. እኔ በዴሪክ ኪድነር ይዘት እጅግ እደሰታለሁ። የእርሱ ሐተታ በዘፍጥረትና መዝሙር፣ በቲንዳሌ ብኪ ተከታታይ ጽሑፍ በረከት ሆኖልኛል። በዚህ መዝሙር ሐተታ መጀመሪያ ላይ እንዲህ ይላል፡
"መዝሙር በአብርሃም ተስፋ ዙሪያ ከተጻፈ፣ እሱ ይባረካልም ለበረከትም ይሆናል፣ በእንደዚህ ዓይነቱ ላይ ደኅና አድርጎ ተገልጿል" (ገጽ 254)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**_መዝሙር፡ 67፡1-7_**

[1]**እግዚአብሔር ይማረን ይባርከንም፥**
**_ፊቱንም በላያችን ያብራ_** **ሴላህ።**
[2]**በአሕዛብ ሁሉ መካከል ማዳንህን፥**
**_መንገድህንም በምድር እናውቅ ዘንድ።_**
[3]**አቤቱ፥ አሕዛብ ያመስግኑህ፥**
**አሕዛብ ሁሉ ያመስግኑህ።**
[4]**ለአሕዛብ በቅን ትፈርድላቸዋለህና፥**
**አሕዛብንም በምድር ላይ ትመራለህና**
**አሕዛብ ደስ ይበላቸው ሐሤትም ያድርጉ።** **ሴላህ**
[5]**አቤቱ፥ አሕዛብ ያመስግኑህ፥**
**አሕዛብ ሁሉ ያመስግኑህ።**
[6]**ምድር ፍሬዋን ሰጠች**
**እግዚአብሔር አምላካችንም ይባርከናል።**
[7]**እግዚአብሔር ይባርከናል፥**
**የምድርም ዳርቻ ሁሉ ይፈሩታል።**

**67፡1** ቁጥር 1 ጸሎት ነው፣ ሁለንተናዊ የመዋጀት መዓዛ ያለው። ያህዌ ይሻል፣ በመልኩና በአምሳሉ የተፈጠሩት ሰዎች ሁሉ (ዘፍ. 1፡26-27) ወደ ኅብረት ይመለሱ ዘንድ፣ በዘፍጥረት 3 ላይ ካለው የአዳምና ሔዋን ዓመጸኝነትና ኃጢአተኝነት ተከትሎ። የዘፍ. 3፡15 ተስፋ ለሰዎች ሁሉ ነው የታዘዘው (እስራኤል የሚባል አልነበረም፣ አብርሃም ዘፍጥረት 12 ላይ እስኪጠራ ድረስ)።

የተጎዳው "አምሳል" ደኅንነት/መታደስ የእግዚአብሔር የማይለወጥ ግብ ሆኗል፣ ከውድቀት ጀምሮ (ማለትም፣ ኢሳ. 2፡2-4፤ 45፡22፤ 52፡10፤ 56፡7፤ ሚኪያስ 4፡1-2)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ መዝሙር 2 መግቢያ ላይ። እሱም የእኔን መሠረታዊ *ሥነ-መለኮታዊ ቅድመ-ግምት* እና *ሥነ-መለኮታዊ ፈርጅ* ያመለክታል!

▣ **"እኛ"** "እኛ" እነማናቸው (ሁለቴ ቁ. 1 ላይ እና ቁ. 6ለ፣ 7ሀ)? ከዘኍልቁ 6 ማጣቀሻ (ማለትም፣ አሮናዊ ባርኮት) እስራኤል ነው ብሎ መገመት ይቻላል (መዝ. 4፡6)፣ ነገር ግን ሌሎቹን ማጣቀሻዎች ተገንዘቡ።

1. ሕዝቦች፣ ቁ. 3፣4ለ፣5ሀ
2. ሕዝቦች ሁሉ፣ ቁ. 3፣5ለ
3. አሕዛብ፣ ቁ. 4ሀ
4. የምድር አሕዛብ፣ ቁ. 4ሐ
5. የምድር ዳርቻ ሁሉ፣ ቁ. 7ለ

እግዚአብሔር የሁሉንም መዳን ይሻል (ዮሐንስ 3፡16-17፤ 4፡42፤ ሐዋ. 2፡17፤ 1 ጢሞ. 2፡4፤ 4፡10፤ ቲቶ 2፡11፤ 2 ጴጥ. 3፡9፤ 1 ዮሐንስ 2፡1-2፤ 4፡9-10)።

▣ **"ሴላህ"** መዝሙር 3፡2 ማስታወሻ እና መግቢያ ለመዝሙር፣ VII ተመልከት።

▣ **"ፊቱንም በላያችን ያብራ"** ይህ የበረከት ቃል፣ የያህዌ አካላዊ መገኘትና ኅብረት የመጣው ከአሮናዊ ባርኮት ነው፣ ከዘኍ. 6፡22-27። ምስያው ዘወትር ይደጋገማል መዝሙር (መዝ. 4፡6፤ 31፡16፤ 80፡3፣7፣19፤ 119፡135)።

**67፡2 "መንገድህ"** ይህ የእግዚአብሔር መንገድ የእርሱን መገለጥ ያመለክታል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር ራዕይ ቃላት መዝ. 1፡2 ላይ። የመዝ. 16፡11ን *ሥነ-መለኮታዊ ትይዩ* ተመልከት።

የመጽሐፍ ቅዱሳዊ የእምነት ጽንሰ-ሐሳብ እንደ መንገድ/ጎዳና ዓይነተኛ ነገር ነው (መዝሙር 1 ተመልከት)። ኢየሱስ እንደ ደጅ እና መንገድ ገልጾታል (ማቴ. 7፡13-27)፣ ግለሰባዊ መቋቋም፣ ክርስቶስ-ተኮር ሕይወትን አስከትሎ (ያዕቆብ 2፡14-26)። ከእኔ ሐተታ፣ ከሐዋ. 9፡2 ከታች ማስታወሻ አከፍበታለሁ።

> ሐዋ.9፡2 "መንገድ" ይህ የቀድሞ የአማኞች መጥሪያ ነው (ዝከ. 19፡9፣23፤ 22፡4፤ 24፡14፣22 እናም 18፡25፣26 ሊሆን ይችላል)። እሱም የብኪ ዳራ አለው፣ ስለ ሕይወት ስልት እምነት የሚናገረው (መዝ. 1፡1፤ 16፡11፤ 119፡105፤ 139፡24፤ ምሳ. 4፡10-19)። ኢየሱስ ይሄንን ጽንሰ-ሐሳብ ተጠቅሟል ማቴ. 7፡14 ላይ፣ እንዲሁም መጠሪያውን ለራሱ ተጠቅሟል፣ ዮሐንስ 14፡6 ላይ። ክርስትና ግላዊ አቋም ነው፣ የየቀኑ ግንኙነትን ተከትሎ።

⊡ **"ምድር"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 1፡2 ላይ። ዐውደ-ጽሑፍ ፍችን ይወስነዋል!

**67፥4** ይህ ቁጥር አሉታዊ ሊሆን አይችልም (ማለትም፣ ፍርድ ብቻ) ምክንያቱም የእግዚአብሔር ፍርድ በጽድቅ ላይ ለአሕዛብ ምክንያት ይሆናል

1. መደሰት
2. በደስታ ለመዘመር
3. በእግዚአብሔር ለመመራት

የአሕዛብ በእግዚአብሔር የመመራት ሐሳብ ትልቅ ጠቀሜታን ይወስዳል፣ ምን ያህል ጊዜ እንደነበር ግንዛቤ በሚገኝበት ጊዜ (ያለፈ፣ የአሁን፣ የወደፊት) ይህ ቃል (ቢዲቢ 634) ለእስራኤል ነው ጥቅም ላይ የዋለው (ዘዳ. 32፡12፤ ነህ. 9፡12፤ መዝ. 5፡8፤ 23፡3፤ 31፡3፤ 43፡3፤ 73፡24፤ 78፡14፣ 53፣72፤ 107፡30፤ 139፡10፤ 143፡10)። እንግዲህ ይኸው መለኮታዊ አመራር ይገኛል፣ ንስሐ ለሚገባው፣ ለሚያምነው፣ ለአሕዛብ ዓለም (ኤር. 16፡ 19)።

**67፥6** የብኪ ኪዳን ተስፋ የግብርና ባርኮቶች ነበሩ፣ ኪዳኑን ለሚታዘዙት ለእነርሱ (ማለትም፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-28)። ይህ ቁጥር የሚያመለክተው ንስሐ የገቡ አማኝ ወገኖችን ነው፣ ከምድር ሕዝቦች መካከል። እሱም የፍጻሜ ዘመን ግፊት አለው።

መጽሐፍ ቅዱስ የሚጀምረው በግብርና በረከት ነው (ማለትም፣ ዔድን ገነት) የሚጨርሰውም በተመሳሳይ ምናብ ነው (ራዕይ 21-22)። ይኸም የሚያመለክተው የኅብረት ስፍራ በእግዚአብሔር እና በሰው መካከል በዔድን ገነት እንደሚመለስ ነው (ማለትም፣ የጸዳችና የታደሰች ምድር)። ይሄም ምናባዊ ይሁን ትንቢታዊ ማወቅ የሚቻልበት መንገድ የለም።

ብዙ ሊቃውንት ይሄንን መዝሙር የሚመለከቱት እንደ መኸር በረከት ነው፣ በዚህ ቁጥር ላይ በመመሥረት። ሆኖም፣ የዩኒቨርሳል ይዘቶች መብዛት ይሄንን አጠራጣሪ ያደርጉታል። ይህ መዝሙር እግዚአብሔር ስላለው መሻት ነው፣ አሕዛብ ሁሉ እሱን እንዲያውቁት (ዝኪ. ቁ. 2) እና እንዲከተሉት (ቁ. 4) እና፣ ብሎም እንዲባረኩ (ቁ. 6)!

**67፥7 "የምድርም ዳርቻ ሁሉ ይፈሩታል።"** ይህ "ፍርሃት" የሚለው ቃል አጠቃቀም፣ (ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432) በመገረም፣ በአክብሮት፣ ፍርሃት ነው። ይህ ሁለንተናዊ ጭብጥ ደግሞ መዝ. 22፡27 እና 33፡8 ላይ ሰፍሯል።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ለማን ነው የተመለከተው?
2. ቁጥር 2 ከሥነ-መለኮት አኳያ እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው ለምድነው? ይህ ጭብጥ ለዚህ መዝሙር የተለየ ነውን?
3. ቁጥር 4ን በገዛ ራስህ ቃላት አብራራ። እሱስ አዎንታዊ ነው አሉታዊ?
4. ሰማይ የታደሰ ምድር ይሆናልን?
5. የዚህ መዝሙር ሥነ-መለኮታዊ ግፊት ለመዝሙር እንግዳ ነውን?

# መዝሙር 68
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የሲና አምላክ የመቅደሱም<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ፤ በመሰንቆ የዳዊት መዝሙር | የእግዚአብሔር ክብር ለእስራኤል ባለው ቸርነት | ቅዱስ ሥርዓት ለበዓል አክብሮት በመቅደስ | ብሔራዊ የድል ዝማሬ | የእስራኤል ክብር ግጥም |
| 68:1-4 | 68:1-3 | 68:1-3 | 68:1-3 | 68:1-2 |
| | | | | 68:3-4 |
| | 68:4 | 68:4 | 68:4 | |
| 68:5-6 | 68:5-6 | 68:5-6 | 68:5-6 | 68:5-6 |
| 68:7-10 | 68:7-10 | 68:7-10 | 68:7-10 | 68:7-8 |
| | | | | 68:9-10 |
| 68:11-14 | 68:11-14 | 68:11-14 | 68:11-14 | 68:11-12 |
| | | | | 68:13-14 |
| 68:15-18 | 68:15-16 | 68:15-16 | 68:15-16 | 68:15-16 |
| | 68:17-18 | 68:17-20 | 68:17-18 | 68:17-18 |
| 68:19-23 | 68:19-20 | | 68:19-20 | 68:19 |
| | | | | 68:20-21 |
| | 68:21-23 | 68:21-23 | 68:21-23 | |
| | | | | 68:22-23 |
| 68:24-27 | 68:24-27 | 68:24-27 | 68:24-27 | 68:24-25 |
| | | | | 68:26-27 |
| 68:28-31 | 68:28-31 | 68:28-31 | 68:28-31 | 68:28-29 |
| | | | | 68:30-31 |
| 68:32-35 | 68:32-35ለ | 68:32-35ሐ | 68:32-35ሐ | 68:32-24ሀ |
| | | | | 68:34ለ-35ሐ |
| | 68:35ሐ | 68:35መ | 68:35መ | 68:35መ |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ሦስተኛው አንቀጽ*
4. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. በዚህ መዝሙር ላይ ወጥ የሆነ (ኅብር ያለው) ጭብጥ ለማግኘት አዳጋች ነው። እሱ ሊሆን የሚችለው የያህዌ ድርጊቶች ስብስብ ነው፣ በእስራኤል በኩል (ማለትም፣ ዘጸአት፣ ድል ማድረግ፣ በኢየሩሳሌም የመቅደስ ምሥረታ)። አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 805) እሱን የሚጠራው "የዝማሬ አምልኳዊ በዓል፣ እሱም የእስራኤልን አምላክ ሕግ ድል አድራጊነት ግርማ" በሚል ነው። ይህ እውነት ከሆነ፣ ይህ መዝሙር ከነህምያ 9 ጋር ይመሳሰላል።

ለ. አንዳንድ ሊቃውንት ይሄንን መዝሙር የሚመለከቱት ያለ ምንም ጭብጥ እንደተቀነባበረ ነው።
1. አየተመት፣ አዲሱ አክስፎርድ ማብራሪያዊ መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 728) የሚለው፣ "ይህ ለትርጓሜ እጅግ አስቸጋሪው መዝሙር ነው፣ እናም አጠቃላይ ስምምነት የለም፣ በፍችውም እንዳጠቃላይ ወይም በበርካታ ዝርዝሮቹም ላይ።"
2. የዩቢኤስ የመዝሙር ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 577) የሚለው፣ "በሁለቱም፣ እንደ ጽሑፍም ሆነ ፍች ይህ መዝሙር እጅግ አስቸጋሪ ነው፣ ከመዝሙራት ሁሉ፣ ለመረዳትና ለመተርጎም። ታሳቢ የሆነ አንድነት በጽሑፉ ላይ የለም።"
3. የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 1353) የሚለው፣ "ሙዳየ ቃላቱ አስራ አምስት ቃላትን ያካትታል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ በየትኛውም ስፍራ የማይገኙ፣ በተጨማሪም ሌሎች ያልተለመዱ ቃላት መካተታቸው እሱን መተርጎም አዳጋች አድርጎታል። በርግጥ፣ አብዛኛው ክፍሉ ግልጽ ሳይሆን ይቀራል፣ እናም ብዙዎች የሚመለከቱት በመዝሙር ላይ እጅግ አስቸጋሪው መዝሙር እንደሆነ ነው።"
4. ለጽሑፉ ቅንብር መላምታዊነት አንደኛው ምክንያት የመለኮት በርካታ ስሞች ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡1 ላይ) ጥቅም ላይ የዋሉትን።
   ሀ. *ኤሎሂም* (ቢ.ዲ.ቢ. 43)፣ ቁ. 1፣2፣3፣4፣5፣6፣7፣8 (ሁለቴ)፣ 9፣10፣15፣16፣17፣18፣21፣24 (ሁለቴ)፣26፣28፣31፣32፣34፣35 (ሁለቴ)።
   ለ. *ያህ* (ቢ.ዲ.ቢ. 43)፣ ቁ. 4፣18
   ሐ. *ኤሎሆ* (ቢ.ዲ.ቢ. 43)፣ ቁ. 8፣28 (የ*ኤሎሂም* ነጠላ)
   መ. *አዶናይ* (ቢ.ዲ.ቢ. 10)፣ ቁ. 11፣17፣19፣20፣22፣32
   ሠ. *ሻዳይ* (ቢ.ዲ.ቢ. 994)፣ ቁ. 14 (የያህዌ ስም ለአባቶች፣ ዘጸ. 6:3)
   ረ. *ኤል* (ቢ.ዲ.ቢ. 42)፣ ቁ. 19፣20 (ሁለቴ)፣ 35
   ሰ. ያህዌ (ቢ.ዲ.ቢ. 217)፣ ቁ. 20፣26
   ሸ. *ንጉሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 572 II)፣ቁ. 24

ሐ. ታሳቢ የፍሬ ሐሳብ ዝርዝር በጭብጦች።
1. ወታደራዊ ድል
   ሀ. ቁ. 1-4 (ስማቸው ያልተጠቀሰ ጠላቶች፣ የምድረ-በዳ መንከራተት ሊሆን ይችላል፣ ቁ. 4ለ)
   ለ. ቁ. 11-14 (ስማቸው ያልተጠቀሰ ነገሥታት፣ ወረራ ያካሄዱ ግን የተሸነፉ)
   ሐ. ቁ. 19-23 (ስማቸው ያልተጠቀሰ ጠላቶች)
   መ. ቁ. 28-31 (ግብፅ)
2. ኪዳናዊ ትኩረት
   ሀ. ዝቅተኞቹን መርዳት፣ ቁ. 5-6
      (1) የሙት ልጆች
      (2) ባል የሞተባቸው
      (3) ደሀ
      (4) ብቸኛ
   ለ. በረከት፣ ቁ. 7-10
   ሐ. ሲና፣ ቁ. 15-18
3. መቅደስ
   ሀ. የንጉሥ እና የእስራኤል ሕዝብ አጀብ ወደ መቅደስ፣ ቁ. 24-27
   ለ. ሕዝቦች ሁሉ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ (ማለትም፣ የመዝሙር 65-68 ጭብጥ) እነርሱም ከመቅደሱ የሚገዙ (ማለትም፣ ኢየሩሳሌም፣ ጽዮን፣ ሞሪያ ተራራ፣ መቅደስ)፣ ቁ. 32-35

ስለዚህ፣ እኔ የምገምተው ይህ መዝሙር የሚገልጸው ወታደራዊ ድል ነው፣ ወደ መቅደስ ከሚደረግ አጀብ (ጉዞ) ጋር፤ ቀኑ ርግጠኝነት የለውም!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 68፡1-4**

**1እግዚአብሔር ይነሣ፥ ጠላቶቹም ይበተኑ፥**
**የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ።**
**2ጢስ እንደሚበንን እንዲሁ ይብነኑ**
**ሰም በእሳት ፊት እንደሚቀልጥ፥**
**እንዲሁ ኃጥኣን ከእግዚአብሔር ፊት ይጥፉ።**
**3ጻድቃንም ደስ ይበላቸው፥ በእግዚአብሔርም ፊት ሐሤት ያድርጉ፥**
**በደስታም ደስ ይበላቸው።**
**4ለእግዚአብሔር ተቀኙ ለስሙም ዘምሩ**
**ወደ ምድረ በዳ ለወጣም መንገድ አድርጉ ስሙ እግዚአብሔር ነው፥**
**በፊቱም ደስ ይበላችሁ በፊቱም ይደነግጣሉ።**

**68፡1-4** ይህ የመጀመሪያ አንጓ በርካታ ቃል ያልተጠናቀቁ አሉት፣ እነርሱም በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ ሊሆኑ ይችላሉ። "ምናልባት..." እና "እን..." የሚሉት ግሦች የዚህ ሰዋሰዋዊ መልክ መለያዎች ናቸው።
1. እግዚአብሔር ይነሣ – ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
2. ጠላቶቹም ይበተኑ – ቢዲቢ 806፣ ኬቢ 918፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
3. የሚጠሉትም ከፊቱ ይሸሹ – ቢዲቢ 630፣ ኬቢ 681፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
4. ኃጥአን ይጥፉ – ቢዲቢ 1፣ ኬቢ 2፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
5. ጻድቃን ደስ ይበላቸው – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
6. በእግዚአብሔርም ፊት ሐሴት ያድርጉ – ቢዲቢ 763፣ ኬቢ 836፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
7. በደስታም ደስ ይበላቸው – ቢዲቢ 965፣ ኬቢ 1314፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*

▣ የእግዚአብሔር ጠላቶች ባሕርይ በተለያዩ መንገዶች እንደተገለጸ ተገንዘብ።
1. ጠላቶች፣ ቁ. 1ሀ – ቢዲቢ 33፣ ኬቢ 38፣ *ቃል* የድርጊት አንቀጽ ("ጠላት የሆኑት")
2. "የሚጠሉት፣" ቁ. 1ለ – ቢዲቢ 971፣ ኬቢ 1338፣ ፔል አንቀጽ
3. ኃጢአተኞች፣ ቁ. 2ሐ – ቢዲቢ 957

እነርሱ "ይበተኑ፣" "ይሸሹ፣" "ይባረሩ፣" "ይቀለጡ፣" "ይጥፉ፣" ጻድቃን ግን
1. ይደሰቱ፣ ቁ. 3ሀ
2. ከፍ ይበሉ፣ ቁ. 3ሀ
3. በደስታ ደስ ይበላቸው፣ ቁ. 3ለ
4. ለእግዚአብሔር ዘምሩ ቁ. 4ሀ – ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ *ቃል ተተኳሪ*
5. ለስሙ ምስጋና ይዘምራሉ፣ ቁ. 4ሀ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ፔል ተተኳሪ
6. ለእርሱም መንገድ አድርጉ፣ ቁ. 4ለ – ቢዲቢ 699፣ ኬቢ 757፣ *ቃል ተተኳሪ*
7. በፊቱም ደስ ይበላችሁ፣ ቁ. 4ሐ – ቢዲቢ 759፣ ኬቢ 831፣ *ቃል ተተኳሪ*

**68፡1 "እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ... ይነሣ"** ይሄንን በሁለት መልኩ መረዳት ይቻላል።
1. ከዙፋኑ ይነሣ፣ ይተገብር ዘንድ
2. የኪዳኑ ታቦት ወደ ጦርነት ይወሰዳል፣ በእስራኤል ሠራዊት ፊት (ዘኁ. 10፡35)

**68፡2** የመሸነፍ በርካታ ዘይቤዎች።
1. እንደሚተን ጢስ
2. በብርቱ ነፋስ ፊት እንዳለ ጢስ
3. በያህዌ ፊት እንደሚቀልጥ ሰም (መዝ. 97፡5፤ ሚኪያስ 1፡4)
4. ይጥፉ (ማለትም፣ እንዲጠፉ ማድረግ፣ ቢዲቢ 1)

**68፡4** ይህ ቁጥር አራት ተተኳሪዎች አሉት፣ የጻድቅን ሥራ የሚገልጹ።
1. ለእግዚአብሔር ይዘምራሉ — የመቅደስ ተግባር
2. ለስሙ ምስጋና ይዘምራሉ — የመቅደስ ተግባር
3. ለእርሱ መንገድ ያዘጋጃሉ— የዝግጁነት ንጉሣዊ ዘይቤ ኢሳ. 35:6-10፤ 40:3-4፤ 57:14፤ 62:10
4. በፊቱ ደስ ይላቸዋል – የመቅደስ ተግባር

የዚህ መዝሙት ኅብራዊ ጭብጥ የቤተ-መቅደስ አምልኮ ነው (ዝከ. 68:5፣24-27፣29፣35)።

▣ ***"ወደ ምድረ-በዳም ለወጣ"*** የያህዌ በደመና ላይ የመራመዱ ጽንሰ-ሐሳብ (ዝከ. ቁ. 33) *የበኣል ጠቃሽ* ነው፣ የከነአናውያን የማዕበል ጣዖት አምላክ ነው፣ እሱም ዝናብ የሚያመጣ። ዘወትር የጣዖት አማልክት መጠሪያዎች ለያህዌ ይሰጣሉ፣ ብቻውን እውነተኛ ለሆነው አምላክ (ዘዳ. 33፡26፤ ኢሳ. 19፡1)።

ኤምቲ "በረሀዎች" አሉት (ቢዲቢ 787) ኬቢ 879 የሚለው ግን "ደመናት" ነው፣ ከዑጋሪቲክ ሥር (መዝ. 104፡3)። ይህም ከዐውደ-ጽሑፉ ጋር በተሻለ ይስማማል አኪጀት፣ አየተመት፣ አእቅ፣ አኢመቅ፣ ጄፒኤስአኤ፣ የተእመቅ፣ መዝ. 18:9-15)።

አመቅ ברע የሚለውን ሥር ይወስዳል (ቢዲቢ 787) "ዓረቢያን" እንደሚጠቅስ (2 ዜና. 17:11፤ 21:16፤ 2:1፤ 26:7)። ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ሐ. 1 ላይ።

LXX ברעמ የሚለውን ሥር ይወስዳል (ቢዲቢ 591 II) ፍችውም "ምዕራብ።"

ታርጉምስ፣ ፔሺታንና ኋለኛውን ኪንግ ጀምስ ተከትሎ ያሉት፣ "ሰማይ" የሚል አላቸው ዝከ. ቁ. 33።

---

***መዝሙር ፡ 68፡5-6***

**5 እግዚአብሔር በቅዱስ ቦታው**
**ለድሀ አደጎች አባት፥ ለባልቴቶችም ዳኛ ነው።**
**6 እግዚአብሔር ብቸኞችን በቤት ያሳድራቸዋል፥**
**እስረኞችንም በኃይሉ ያወጣቸዋል**
**ዓመፀኞች ግን በምድረ በዳ ይኖራሉ።**

---

**68፡5-6** እግዚአብሔር ለእነርሱ ሆኖ የሚሠራውን ሰዎች ዓይነቶች ተገንዘብ (ማለትም፣ ዘጸ. 22፡23)።

1. ወላጅ አልባዎች – ዘጸ. 22:22፣ ዘዳ. 14:29፣ 24:17፣መዝ. 146:9፣ ኢሳ. 1:17፤ ኤር. 7:6፤ ያዕቆብ 1:27
2. ባል የሞተባቸው – ዘጸ. 22:22፤ ዘዳ. 14:29፤ 24:17፤ መዝ. 146:9፤ ኢሳ. 1:17፤ ኤር. 7:6፤ ያዕቆብ 1:27
3. ብቸኞች – ቢ.ዲ.ቢ. 402፣ ኬ.ቢ. 405፣ ከዓረብኛ "ብቻ መሆን"
4. ደሀ – ኢዮብ 31:16-20፤ መዝ. 69:33 ( "ባርያ፣" ቢ.ዲ.ቢ. 64)፤ ያህዌ "ለችግረኛ" ይሰጣል (ቢ.ዲ.ቢ. 776) ቁ. 10 ላይ

ቁጥር 6 ላይ በሂደት ላይ ያለው የእግዚአብሔር ቀጣይነት ያለው ድርጊት ላይ ልዩነት እንዳለ ተገንዘብ

1. ቤት ይሠራል ("መኖርያን ያመቻቻል") – ቢ.ዲ.ቢ. 442፣ ኬ.ቢ. 444፣ ሂፊል አንቀጽ
2. ይመራል – ቢ.ዲ.ቢ. 422፣ ኬ.ቢ. 425፣ ሂፊል አንቀጽ

ለድሀና ለችግረኛው ከቋሚ መኖርያ ጋር እንደተቃረነ (ቢ.ዲ.ቢ. 1014፣ ኬ.ቢ. 1496፣ ቃል የተጠናቀቀ) ከእምቢተኞች/ዓመጸኞች፣ እነርሱም የማይለወጡ (ቢ.ዲ.ቢ. 710፣ ኬ.ቢ. 770፣ ቃል አንቀጽ) እናም "በደረቅ ምድር" ከሚኖሩ (ቢ.ዲ.ቢ. 850፣ ብኪ ላይ እዚህጋ ብቻ፣ ነገር ግን የተለመደ ምስያ ነው፣ ለያህዌና ለፍርድ ምልክቱ አለመገኘት መዝ. 78:17፤ 107:34፣40)።

▣ ***"ዓመጸኞች ግን ወደ ምድረ-በዳ ይኖራሉ"*** አንዱ ሊደነቅ ይችላል እነዚህ ዓመጸኞች ቁጥር 1-2 ላይ ከተጠቀሱት ጋር ተመሳሳይ ሰዎች ለመሆናቸው። ነገር ግን የቁጥር 5-6 ዐውደ-ጽሑፍ የሚያመለክተው እነርሱ ያልታመኑ ኪዳናዊ እስራኤላውያን መሆናቸውን ነው።

ብልጽግና የታመኑ ተከታዮች መለያ መሆኑንና፣ የዝናብ እጥረት ደግሞ የዓመጸኞች ምልክት መሆኑን። ይህ ዓይነቱ ሥነ-መለኮት፣ ይኸውም በኪዳን ታዛዥነት ላይ የተመሠረተው (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30) "ሁለቱ መንገዶች" በሚል ይታወቃል (ዝከ. 68:7-10፤ ዘዳ. 30:15-20፤ መዝሙር 1)።

| |
|---|
| ***መዝሙር ፡ 68፡7-10***<br>**[7]አቤቱ፥ በሕዝብም ፊት በወጣህ ጊዜ፥**<br>**በምድረ በዳም ባለፍህ ጊዜ፥ ሴላህ**<br>**ምድር ተናወጠች፥**<br>**[8]ከሲና አምላክ ፊት፥**<br>**ከእስራኤል አምላክ ፊት ሰማያትም አንጠበጠቡ።**<br>**[9]አቤቱ፥ የሞገስን ዝናብ ለርስትህ አዘነብህ፥**<br>**በደከመም ጊዜ አንተ አጸናኸው።**<br>**[10]እንስሶችህ በውስጡ አደሩ**<br>**አቤቱ፥ በቸርነትህ ለድሆች አዘጋጀህ።** |

**68፡7-10** አጽንዖቱ ቀጥሏል በ"ሁለቱ መንገዶች" ላይ ያለው ። ይህ አንጻ የሚያደባልቀው

1. የምድረ-በዳ መንከራተት ዘመን (ማለትም፣ እስራኤል በያህዌ የተመራበት፣ በደመና፣ ዘጸ. 13:21፤ 14:19፣24፤ መዝ. 78:14፤ 105:39) እናም በተአምራዊ የተሰጣቸው (ማለትም፣ ውኃ፣ መና፣ ድርጭት)
2. የተስፋይቱ ምድር የግብርና በረከት (ማለትም፣ የዮርዳኖስ ዳርቻ እና ከነአን)

**68፡7 "በሕዝብህም ፊት በወጣህ ጊዜ"** ይህ "ለቅዱስ ጦርነት" ፈሊጥ ነው። ጦርነቶቹ የያህዌ ድሎች ነበሩ። እሱ በሕዝቡ ፊት ወደ ጦርነት ይሄድ ነበር (መሳ. 4:14፤ 2 ሳሙ. 5:24)። ይህ ዘወትር ተምሳሌታዊ የሚሆነው የኪዳኑን ታቦት ሌዋውያን ተሸክመውት በሠራዊቱ ፊት መሄዳቸውን ነው።

▣ **"በምድረ በዳም ባለፍህ ጊዜ፥"** ይህ የምድረ-በዳውን የመንከራተት ዘመን ያመለክታል (መሳ. 5፡4-5)። ያህዌ እስራኤልን በሚያስፈልገው ሁሉ ይጠብቀው፣ ይመራው፣ ይሰጠው ነበር አርባ ዓመት በተንከራተተበት ጊዜ፣ ወደ ከነአን ከመግባታቸው በፊት፣ ባለማመናቸው ምክንያት (ዘኍልቍ 13-14)። ያህዌ በዚህ ሰዓት ለእስራኤል እጅግ ይገኝላቸው ነበር፣ ማለትም ኋለኞቹ ራቢዎች "የያህዌ እና የእስራኤል የጫጉላ ጊዜ" ብለው የሚጠሩት።

▣ **"ሴላህ"** መዝሙር 3፡2 ማስታወሻ እና መግቢያ ለመዝሙር VII ተመልከት።

**68፡8 "ምድር ተናወጠች"** ይህ ሁለቱም ነው፣ የያህዌ መገኘት ዘይቤ (ኢዩኤል 2:10፤ማቴ. 27:51) እና ጥሬአዊ አካላዊ የእርሱ መገኘት መገለጫ (ዘጸ. 19:16-18፤ መሳ. 5:4-5)።

▣ "የሲና አምላክ" (ማለትም፣ የሕግን መስጠት፣ ዘጸአት 19-20) "ከእስራኤል አምላክ" ጋር ትይዩ መሆኑን ተገንዘብ። ደራሲው በርካታ ስሞችን ለ "እግዚአብሐር" ተጠቅሟል (ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ለ፣ 4 ላይ)። የእስራኤል የተለየ መሆን የያህዌ መገኘት ነው (አሀዳዊነት) እናም እርሱ ራሱን መግለጡ፣ በድርጊት፣ በተስፋ፣ እና በተጻፈ መገለጥ (ብኪ)።

**68፡9 "ርስትህ"** ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 635) ሊያመለክት የሚችለው

1. የኪዳኑን ሕዝብ (ዘዳ. 32:9፤ 1 ነገ. 8:51፤ ኢዩኤል 3:2፤ ኤር. 10:16)
2. የከነአን ምድር (መዝ. 79:1፤ ኤር. 2:7)

"ምድር" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 75፣ ኬ.ቢ. 90) ጥቅም ላይ የዋለው ለመላው ዓለም ነው (ዘጸ. 19:5) ነገር ግን በተለይ ለከነአን (ሌዋ. 25:23፤ ዘዳ. 32:43፤ 2 ዜና. 7:20፤ ኢሳ. 14:2፣25፤ሕዝ. 36:5)። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 1:2 ላይ።

**68:10**

**ኢአመመቅ** **"እንስሶች በውስጡ አደሩ"**
**አኪጀት** **"ማኅበረ ምዕመናንህ በውስጡ አደሩ"**
**አየተመት** **"መንጋህ በውስጡ ማደሪያ አገኙ"**
**አእቅ** **"እሕዝብ እዚያ መኖሪያቸውን አደረጉ"**
**LXX** **"እንስሶችህ በውስጡ አደሩ"**
**አኢመቅ** **"ወገኖችህ መኖርያ አገኙ"**
**ጀፒኤስአኤ** **"ነገዶችህ መኖርያቸውን እዚያ አደረጉ"**

LXX ይሄንን የሚተረጉመው "እንስሶች" በሚል ነው፣ ነገር ግን አንስታይ (ሴቴ ጾታ) (ቢዲቢ 312) ፍችውም "ተጓዳኝ ማኅበረሰብ" (2 ሳሙ. 23፡13፤ 1 ዜና. 11፡15)።

---

***መዝሙር ፡ 68፡11-14***

[11]*እግዚአብሔር ቃሉን ሰጠ*
*የሚያወሩት ብዙ ሠራዊት ናቸው።*
[12]*የሠራዊት ነገሥታት ፈጥነው ይሸሻሉ*
*በቤትም የምትኖር ምርኮን ተካፈለች።*
[13]*በርስቶች መካከል ብታድሩ፥*
*ከብር እንደ ተሠሩ እንደ ርግብ ክንፎች፥*
*በቅጠልያ ወርቅም እንደ ተለበጡ ላባዎችዋ ትሆናላችሁ።*
[14]*ሰማያዊ ንጉሥ በላይዋ ባዘዘ ጊዜ፥*
*በሰልሞን ላይ በረዶ ዘነበ።*

---

**68፡11-14** ይህ አንጓ እንደ ቁ. 1-4 እና 19-23 ወታደራዊ ጭብጥ አለው። በቁጥር 11ለ እና 12ለ ምክንያት እሱ ሊያመለክት የሚችለው (1) የኢያሱ ከነአንን ማሸነፍ ወይም (2) የከነአን/እስራኤል ወረራ፣ እሱም ድል የተነሣበት ነው።

**68፡11-12** ይህም የሚያመለክተው መለኮታዊ-ሰጥ የድል ዜና ነው። የተጠቀሱት ሴቶች፣ እነርሱም ዜናውን ያመጡት ቁጥር 12 ላይ ተመዝግቧል። በወታደራዊው ድል የተደሰቱት ሴቶችና፣ በእግዚአብሔር ድርጊት እልል የሚሉት ሴቶች ደግሞ "በማርያም መዝሙር" ላይ በዘጸ. 15፡20-21 ተመዝግበዋል።

**▣**
**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"በቤትም የምትኖር"**
**አየተመት፣ አእቅ፣**
**የተእመቅ** **"በቤት ያሉ ሴቶች"**
**አኢመቅ** **"በቤት ያለች መልካም ሴት"**
**ጀፒኤስአኤ** **"የቤት እመቤት"**

ኤምቲ "መሰማሪያ" የሚል አለው (ቢዲቢ 627 II) ነገር ግን ሁሉም የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ሥሩን ወደ "ሴቶች" ቀይረውታል።

1. መሰምሪያዎች – נוה
2. ሴቶች – נוצה

**68፡13** ይህ ቁጥር መረዳት ያገኘው በበርካታ መንገዶች ነው።

1. ርግብ (ዝከ. ቁ. 13ለ-ሐ) የያህዌ ስም ነው፣ እንደ ሻዳይ (ማለትም፣ ሁሉን ቻይ) - አኢመቅ
2. እሱም ሽሙጣዊ ጠቃሽ ነው፣ አንዳንዶች ወደ ዘመቻ የአለመሄዳቸውን ሐቅ ለማመልከት (ማለትም፣ 13ሀ፣ አእቅ፤ መሳ. 5፡15-16)
3. እሱም የድል አድራጊው እስራኤል መጥቀሻ መንገድ ነው
4. እሱም የጦርነት ምርኮ ክፍል ነው (ማለትም፣ የተያዘ የቀለጠ/ቅርጽ የወጣለት ጌጥ፣ ከአስታር፣ አስታሮት አምልኮ ጋር ሊያያዝ የሚችል)
5. የሴቶች መልእክተኞች አለባበስን የሚጠቅስ፣ ቁጥር 11 ላይ ያለው (ኪንድነር፣ ቲንዳሌ ኮሜንተሪ፣ ገጽ 259)
6. የጦርነት ዓርማ፣ የሚሸሽ ሠራዊት (አይቪፒ የመጽሐፍ ቅዱስ ዳራ ኮሜንተሪ፣ ገጽ 538)
7. የርግቦች መለቀቅ የድል አከባበር ክፍል ነበር (ኤፍ. ኤፍ. ብሩስ፣ ለጥያቄዎች መልሶች፣ ገጽ 23-24)

**▣ "የበጎች በረት"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 1046፣ ኬቢ 1637) ያልተለመደ ነው። ትርጉሙም የተመሠረተው መሳ. 5፡16 ላይ ነው። ተመሳሳይ ቃልም ሕዝ. 40፡43 ላይ ይገኛል፣ "መንጠቆ" በሚል የተተረጎመ። ፍችውም የሚሆነው "የማብሰያ እሳት" ወይም "የማብሰያ ማሰሮ" ነው (ቢዲቢ 1046)።

**68፡14 "ሰማያዊ ንጉሥ"** ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ለ፣ 4።

**▣**
**አአመመቅ፣ አየተመት** **"እዚያ"**
**አኪጀት** **"በእርሱም"**

ኤምቲ አንስታይ (ሴታዊ) መስተጻምር አለው (ቢዲቢ 88) እሱም ተመልሶ ከቁጥር 10 ጋር የሚያያዝ (ማለትም፣ የያህዌ ማኅበረሰብ የሚኖርበት ርስት ያለበት ስፍራ)።

▣ **"ሰልሞን"** ይህ ሴኬም አጠገብ ያለ ስፍራ ነው (መሳ. 9፡48)። ቢዲቢ የሚለው፣ እሱ የሚያመለክተው ከዮርዳኖስ በስተምስራቅ ያለውን ተራራ ነው። በዚህ ምክንያት ነው "ባሳን" የሚለው ስም ቁ. 15 ላይ ያለው።

አኢመቅ እሱን የሚተረጉመው እንደ "ጥቁር ተራራ" በሚል ነው፣ ከአካድያን ሥር የተነሣ፣ ከአንደኛው የዳዊት ሰው፣ ከቢንያም ነገድ ጋር በተያያዘ (2 ሳሙ. 23፡28)።

ኤቢዲ (ገጽ 1039) ሦስተኛ ሐሳብ ይሰነዝራል፣ ከዓረብኛ ሥር እንደመጣ፣ ፍችውም "ብርሃን" ወይም "አብረቅራቂ" የሆነ።

"የበረዶ መውረድ" የሚለው ማጣቀሻም ደግሞ ችግር ያለው ነው። እሱም ሊያመለክት የሚችለው

1. መለኮታዊ ድርጊት፣ በጦርነት ጊዜ፣ መሳፍንት 4-5 ላይ እንዳለው ዝናብ
2. በዘይቤአዊ አገላለጽ የተሸነፈን ስፍራ ጨው መዝራት (መሳ. 9፡45)
3. በዘይቤአዊ አገላለጽ የሞቱ ወታደሮች የገረጡ አጥንቶች (አይዲቢ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 933)
4. የወራሪዎች ድል መሆንን ታሪካዊ ጊዜ መጥሪያ መንገድ
5. "በረዶ መውረድ" የሚለው ግሥ ሂፋል ተጽዕኖዊ ነው፣ በመልኩ፣ ስለዚህ፣ "በሰልሞን ላይ በረዶ ይዝነብ" (ማለትም፣ ትንቢታዊ ምልክት፣ ለመለኮታዊው ድል)
6. የጠላት የጦር መሣርያ በምድር ላይ ተጋደመ፣ እነርሱ ጥለውን ሲሸሹ (አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 806)

## መዝሙር ፡ 68፡15-18

**15የእግዚአብሔር ተራራ የለመለመ ተራራ ነው**
**የጸና ተራራና የለመለመ ተራራ ነው።**
**16የጸኑ ተራራዎች ለምን ይነሣሉ?**
**እግዚአብሔር ይህን ተራራ ያድርበት ዘንድ ወደደው**
**በእውነት እግዚአብሔር ለዘላለም ያድርበታል።**
**17የእግዚአብሔር ሰረገላዎች የብዙ ብዙ ሺህ ናቸው**
**ጌታ በመቅደሱ በሲና በመካከላቸው ነው።**
**18ወደ ላይ ዓረግህ፥ ምርኮን ማረክህ፥**
**ስጦታንም ለሰዎች ሰጠህ፥**
**ደግሞም ለዓመፀኞች በዚያ ያድሩ ዘንድ።**

**68፡15-18** ይህ አንጓ ስለ ሲና ተራራ ነው (ማለትም፣ ኮሬብ ተራራ) እንደ እግዚአብሔር ልዩ ማደሪያ ስፍራ። የሌሎች ሕዝቦች ሌሎች ተራራዎች ይቀናሉ (ዝኪ. ቁ. 16)።

**68፡15**

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **አኢመቅ፣ LXX** | **"የእግዚአብሔር ተራራ"** |
| **አየተመት፣ አእቅ** | **"ጽኑ ተራራ"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"ባለ ግርማ ተራራ"** |
| **የተእመቅ** | **"ከፍ ያለ ኮረብታ"** |

የዕብራይስጡ ቃል ኤሎሂም (ቢዲቢ 43) በተጠናከረ መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል (ቁ. 2ሐ፣ ኢዮብ 1፡16)።

ይኸው ተመሳሳይ ተራራ "ባለ ብዙ ጫፎች ተራራ" ተብሎ ይጠራል፣ በቀጣዩ የቅኔ ስንኝ። ይህ ቃል (ቢዲቢ 148፣ ኬቢ 174) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ። እሱም የሚለው

1. ብዙ ጫፎች (ማለትም፣ የተራራ ጫፍ)
2. ክብ ጫፍ (ዐምባ)

**68፡16ለ፣ሐ** ዘወትር የያህዌ ቋሚ የመኖርያ ስፍራ የኪዳኑ ታቦት ነው፣ እሱም በኢየሩሳሌም በሞሪያ ተራራ ላይ ሊያድር የመጣ (ዘዳ. 12፡5፤ መዝ. 87፡1-2፤ 132፡13-14)፣ እዚህ ግን የምንናገረው ስለ ዘጸአት ነው። ያህዌ ራሱን የገለጠው በሲና ተራራ/ኮሬብ ተራራ ላይ ነው (ዘጸአት 19-20)፣ እዚያም ለሙሴ ሕግን የሰጠበት፣ የኪዳን ታቦት ከመኖሩ በፊት።

▣ **"በቅናት ይመለከታሉ"** ይህ ሰዋዊ ዘይቤ የሆነ የሚቀኑት የባሳን ተራሮች ናቸው። ግሡ (ቢዲቢ 952፣ ኬቢ 1280፣ ፔል ያልተጠናቀቀ) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ። እሱም በተመሳሳይ መንገድ ጥቅም ላይ ውሏል መክብብ 14፡22 ላይ ("በማድባት መቃኘት")።

**68፡17** የዚህ ቁጥር ምስያ የሚጠቅሰው ዘዳ. 33፡2-5ን ነው፣ እዚያም ያህዌ ከቅዱሳን መላእክቱ አጀብ ጋር ወደ ሲና መምጣቱን የሚጠቅስ (ዳን. 7፡10፤ ራዕ. 5፡11)።

ያህዌ ሲና ተራራን ከእስራኤል ጋር እንደ መገናኛ ስፍራ ይጠቀማል፣ ለኪዳን ማበጃ መገለጥ፣ እሱ ግን የሞሪያ ተራራን በኢየሩሳሌም ነው የመረጠው፣ እንደ መገኛው ስፍራ (ማለትም፣ የኪዳኑ ታቦት) እዚያ በቋሚነት ለመኖር (ዝኪ. ቁ. 16)።

▣ **"የብዙ ብዙ ሺህ"** ይህ የዕብራይስጥ አወቃቀር ነው የቢዲቢ 48 እና 1041። ሁለተኛው ቃል እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ። ቢዲቢ እሱን "ተደጋጋሚ" ወይም "የእጥፍ እጥፍ" በሚል ይገልጸዋል። ዐውደ-ጽሑፉና ትይዩው ቃሉን ለመግለጽ ያግዛል።

**68፡18** ከዐውደ ጽሑፍ አኳያ ይህ የሚያመለክተው እግዚአብሔርን ነው

1. ወደ ሲና ተራራ ጫፍ መሄዱ

2. እንደ ወታደራዊ ዘይቤ ለድል አድራጊው የሚደረግ ክፍያ

ጳውሎስ ይሄንን ቁጥር ኤፌ. 4:8 ላይ ጠቅሶታል፣ ነገር ግን የታርጉም ትርጉም "ይቀበላል" የሚለውን "ይሰጣል" በሚል ይቀይረዋል። ይህም የኤምቲን ትርጉም ከመሠረቱ ይቀይረዋል። ፔሺታ አለው

"ለሰዎችም ስጦታ ሰጠህ፤ ዓመጸኞች ግን በእግዚአብሔር ፊት አይኖሩም" የሚል።

በርግጠኝነት መሆን የሚችለው የኤምቲ አንድምታ፣ እግዚአብሔር የአሕዛብን ስጦታ ተቀብሎ ለሕዝቡ እንደሚያከፋፍል ነው (ግሊሰን አርከር የመጽሐፍ ቅዱሳዊ አዳጋቾች ኢንሳይክሎፔድያ፣ ገጽ 404-405 ተመልከት)።

ራቢዎች መዝሙር 68ን የሚመለከቱት ያህዌ ሕግን ለሙሴ በሲና ተራራ ከመስጠቱ ጋር በተያያዘ ነው። እነርሱ "መቀበል/መስጠት"ን የሚተረጉሙት በንቁ መልኩ የሙሴን ሕግ እንደሚጠቅስ ነው፣ ጳውሎስ ግን እሱን የተመለከተው በክርስቶስ እንዳለ አዲስ ሕይወት ነው። እሱ ቤተ ክርስቲያኑን በአዲስ ራዕይ አስታጥቋታል (ጂ.ቢ. ኬርድ፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋና ምናባዊነት*፣ ገጽ 170)።

በቁጥር 15-18 ዐውደ-ጽሑፍ፣ ቁጥር 18 የያህዌን "ቅዱስ ጦርነት" ማመልከት ይኖርበታል፣ እዚያም የእስራኤል ጠላቶች፣ ሁለቱም በመሸጋገሪያ ላይ ያሉት (ማለትም፣ የምድረ-በዳ መንከራተት) እና የከነአን ድል ላይ፣ ተሸንፈዋል። ይህም "የሙሴ ባርኮት" ጠቃሽ ሊሆን ይችላል፣ ዘዳግም 33 ላይ፣ ይኸውም እስከ ኋለኛው ድል እና በከነአን ከመኖር ጋር የተራዘመ።

**መዝሙር ፡ 68፡19-23**

**[19]እግዚአብሔር አምላክ ቡሩክ ነው እግዚአብሔር በየዕለቱ ቡሩክ ነው**
**የመድኃኒታችን አምላክ ይረዳናል። ሴላህ።**
**[20]አምላካችንስ የደኅንነት አምላክ ነው**
**ከሞት መውጣትም ከእግዚአብሔር ነው።**
**[21]ነገር ግን እግዚአብሔር የጠላቶቹን ራስ፥**
**በኃጢአት የሚሄድንም የጠጉሩን አናት ይቀጠቅጣል።**
**[22]እግዚአብሔር እንዲህ አለ፦ ከባሳን አመጣቸዋለሁ፥**
**ከባሕርም ጥልቅ እመልሳቸዋለሁ፥**
**[23]እግሮችህ በደም ይረገጡ ዘንድ፥**
**የውሾችህ ምላስ በጠላቶች ላይ ይሆን ዘንድ።**

**68፡19-23** "ባሳን" ቁጥር 15 እና ቁጥር 22 ላይ ከመጠቀሱ የተነሣ፣ ወታደራዊ ነክ በሆኑት አንጓዎች መካከል፣ ቁጥር 11-14 እና 19-23 ግንኙነት መኖር አለበት። በርካታ ግልጽ የሆኑ እውነቶች አሉ።

1. እግዚአብሔር ከእስራኤል ጋር ነው
2. እግዚአብሔር ከጠላቶቻቸው ያድናቸዋል።

ይህ አንጓ ሦስት የመለኮት ስሞችን ይጠቀማል (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡1 ላይ)።

1. *አዶናይ*፣ ቁ. 19፣20፣21
2. *ኤል*፣ ቁ. 19ለ (ሁለቴ)
3. *ያህዌ*፣ ቁ. 20

**68፡19 "በየዕለቱ ሸክማችንን የሚሸከምልን"** ይሄ የሚገልጸው

1. የያህዌን ቋሚ መገኘት፣ ከእስራኤል ጋር
2. የእስራኤል ቋሚ ፍላጎት አዳኝ/ደኅንነት/ማዳን (መንፈሳዊ እና/ወይም ሥጋዊ፣ መዝ. 65፡5)

ያህዌ የራሱን የሚሸከምበት ሐቅ መዝ. 55፡22፤ ኢሳ. 46፡4።

**68፡20-23** እነዚህ ቁጥሮች አጽንዖት የሚሰጡት የያህዌን ማዳን ነው፣ የእስራኤልን ሠራዊት (ጥቂቶች ሞተዋል ብዙዎች ግን ድነዋል)። ጠላቶቻቸው ሊሮጡ ይችላሉ፣ ነገር ግን አያመልጡም (ዝከ. ቁ. 22፤ አሞጽ 9፡1-4)።

ቁጥር 23 የመሸነፍና የኀፍረትን ፈሊጥ ይዟል።

1. እግሮችህ በደም ይረገጡ (መዝ. 58፡10፤ በከነአን ሥነ-ጽሑፍ የተለመደ ፈሊጥ፣ ለበአልና አናዝ ጥቅም ላይ የዋለ)
2. ውሾች የሞቱ የጠላት ወታደሮችን ይበላሉ (1 ነገ. 21፡19፤ ኤር. 15፡3)

**68፡21 "የጠጉር አናት"** ይህ ለሰው የራስ ቆዳ ምስያ ነው (ዘዳ. 32፡42)። ረጅም ፀጉር በብኪ ለእግዚአብሔር የመሰጠት ተምሳሌት ነው (ዘኍልቁ 6)፣ እዚህጋ ግን ለተሸነፉ ጠላቶች ነው፣ ይኸውም ለጣዖት አምልኮ መሰጠታቸውን ያሳያል፣ ለያህዌ እውቅና መስጠት እምቢ ብለው።

**68፡22 "ከባሳን"** "ባሳን" ምን እንደሆነ ለማወቅ አዳጋች ነው (ቢዲቢ 143፤፣ בָּשָׁן ) ሊሆን የሚችለውም

1. ከቁጥር 15 ጋር የሚያያዝ፣ እንደ መልክዓ ምድራዊ ስፍራ
2. የታረመ בָּשָׁן ፣ የዑጋሪቲክ ሥር ለ "እፉኝት" እሱም ከ "ባሕሩ ጥልቆች" ጋር ትይዩ የሆነ፣ በቀጣዩ ስንኝ ላይ (አአመቅ፣ አሞጽ 9፡3፣ እዚያም ተመሳሳይ ትይዩነት የተከሰተበት ከዕብራይስጡ ቃል "እፉኝት" ጋር)። "ጥልቆች" ደግሞ ከዘጸአት ጋር ይያያዛሉ፣ ያህዌ ባሕሩን የከፈለበትና የፈርዖን የተመረጡ ዘቦች የሰጠሙበት (ዘጸ. 15፡5፤ ነህ. 9፡11)።

**መዝሙር ፡ 68፡24-27**

**[24]የአምላኬ የንጉሥ መንገድ በመቅደሱ፥**
**አቤቱ፥ መንገድህ ተገለጠ።**

**[25]አለቆች ቀደሙ፥ መዘምራንም ተከተሉ**
**ከበሮን በሚመቱ በቈነጃጅት መካከል።**
**[26]እግዚአብሔርን በጉባኤ፥**
**ጌታችንንም በእስራኤል ምንጭ አመስግኑት።**
**[27]ወጣቱ ብንያም በጕልበቱ በዚያ አለ፥**
**ገዦቻቸው የይሁዳ አለቆች**
**የዛብሎን አለቆችና የንፍታሌምም አለቆች።**

**68፡24-27** ይህ አንጓ የሚገልጸው ወደ መቅደስ የሚደረገውን የአጀብ ጉዞ ነው። ታቦቱም ሊኖር ይችላል፣ ወደ ጦርነት የተወሰደው፣ ሲመለስ። በአጀቡ ውስጥ የተጠቀሱ ወይም የተመለከቱ በርካታ ወገኖች አሉ።

1. የእስራኤል ንጉሥ እንደ ያህዌ ተወካይ፣ እውነተኛው ንጉሥ
2. ሌዋውያን ዘማሪዎች እና ሙዚቀኞች
3. ቆነጃጅት ከበሮ እየመቱ (ዘጸ. 15:20፤ መሳ. 11:34፤ ኤር. 31:4)
4. አስራ ሦስቱ ነገዶች በተወካዮቻቸው
   ሀ. ቢንያም
   ለ. ይሁዳ
   ሐ. ዛብሎን
   መ. ንፍታሌም

**68፡24**
**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"አይተዋል"**
**አየተመት** **"ታይተዋል"**
**አእቅ** **"በሁሉም ታይተዋል"**
**አኢመቅ** **"ሁሉም እንዲመለከቱ"**
**ጄፒኤስኦኤ** **"ሰዎች አዩ"**

ጥያቄው ማን ይመለከታል ነው። እሱ እስራኤላዊ ምዕመን ወይም ተቃዋሚ ሕዝቦች ሁሉ ናቸውን? አንጓው የሚያመለክተው እስራኤል ሲሆን ነገር ግን መዝሙሩ እንዳጠቃላይ የሚያመለክተው "አሕዛብን" ነው (ዝከ. ቁ. 28-31፣ 32-35)።

◘ **"የአጀብ ጉዞ"** ቃሉ (ቢዲቢ 237) እዚህጋ ብቻ ነው ጥቅም ላይ የዋለው ለ
1. የእስራኤል ሰዎች ወደ መቅደስ የመጡ
2. መለኮት ወደ መቅደስ ሲመጣ

◘ **"ንጉሤ"** የመጀመሪያው ተለይቶ የተጠቀሰው ለያህዌ ነው፣ እንደ ንጉሥ 1 ሳሙ. 8፡4-9።

◘ **"መቅደስ"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 871) ጥቅም ላይ የዋለው
1. ቅዱስ ተብለው የተለዩ ስፍራዎች፣ በእግዚአብሔር መገኘት
2. የማደሪያው ድንኳንና አካባቢው
3. መቅደሱና የአካባቢው ስፍራዎች
4. ኢየሩሳሌምና ኮረብታዎቿ

**68፡26 "እግዚአብሔርን ባርኩ"** ይህ ፒይል ተተኳሪ ነው። እስራኤል ያህዌን ማመስገን ይገባዋል፣ ስለ ባሕርዩና ስለ ድርጊቶቹ!

◘ **"የእስራኤል ምንጭ"** ይህ ያልተለመደ ሐረግ ነው። እሱም የያህዌን ጥሪ የሚጠቅስ ይመስላል፣ አባቶችንና የእሱም ለመካን ሚስቶቻቸው ልጆችን በመስጠት የባረከበት። ብቸኛው ታሳቢ ዘወርዋራ ትይዩ ማጣቀሻ የሚገኘው ኢሳ. 48፡1 ላይ ነው።

**68፡27** ብዙ ግምቶች አሉ፣ ለምን ጥቂት ነገዶች ብቻ እንደተጠቀሱ። ሦስት ታሳቢዎች ያሉ ይመስለኛል።
1. እነርሱ ሞላውን የተስፋውን ምድር ይወክላሉ
   ሀ. ይሁዳ እና ቢንያም በደቡብ (ማለትም፣ ይሁዳ)
   ለ. ዛብሎን እና ንፍታሌም በሰሜን (ማለትም፣ እስራኤል)
2. እነርሱም የያዕቆብን ሚስቶች ይወክላሉ (ማለትም፣ የ13 ነገዶች ምንጭ)
   ሀ. ራሔል- ቢኒያም
   ለ. ልያ
      (1) ዛብሎን
      (2) ይሁዳ
   ሐ. ባላ - ንፍታሌም
   መ. ዘለፋ - የተጠቀሰ ልጅ የለም
3. እነርሱ የሚወክሉት ከአነስተኛው ነገድ ወደ ትልቁ ነው

◘ **"ወጣቱ"** ኤምቲ "ከእነርሱ ትንሹ" የሚል አለው (ቢዲቢ 859 I)። ይህም ማለት የሚሆነው

1. ቢንያም የራሔል ትንሹ ልጅ
2. አነስተኛው ነገድ፣ ነገር ግን የእስራኤል የመጀመሪያው ንጉሥ፣ ሳኦል ከዚያ ነው የመጣው

▣
**አአመመቅ** ***“በአጀባቸው”***
**አኪጀት** **“በየወገናቸው”**
**አየተመት** **“በአካል”**
**አእቅ** **“በየወገናቸው ”**
**አኢመቅ** **“በብሩኅ ቀለም ልብስ ተጎናጽፈው”**
**ጀፒኤስአኤ** **“የሚያዛቸው”**

ኤምቲ רגמתם የሚል አለው (ቢዲቢ 920)፣ እሱም ሊያመለክት የሚችለው

1. רגם – በድንጋይ መግደል (“የድንጋይ ወገራ፣” מרגמה ፣ ቢዲቢ 920)

2.רגמה – የድንጋይ ክምር ወይም የሰዎች ስብስብ (ቢዲቢ 920)

3 רגשה – የሰዎች ስብስብ (ቢዲቢ 921)

አኢመቅ ቃሉን ያርመዋል (1) ወደ ברקמתם ፣ “ያሸበረቀ የእጅ ሥራ” (ቢዲቢ 140) ወይም (2) “ባለ ብዙ ኅብረ-ቀለም፣” רקמה (መዝ. 45:13ለ-14ሀ)። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ. 293) ለ “ሰዎች ስብስብ” “ለ” ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ)፣ ይህ ግን ስለ ሥሩ የተለየ አይደለም (ማለትም፣ ቁ. 2 ወይም ቁ. 3)።

## መዝሙር ፡ 68፡28-31

[28]**አቤቱ፥ ኃይልህን እዘዝ አቤቱ፥**
**ይህንም ለእኛ የሠራኸውን አጽናው።**
[29]**በኢየሩሳሌም ስላለው መቅደስህ**
**ነገሥታት እጅ መንሻን ለአንተ ያመጣሉ።**
[30]**በሸምበቆ ውስጥ ያሉትን አራዊት፥**
**በአሕዛብ ውስጥ ያሉትን የበሬዎችንና የወይፈኖችን ጉባኤ ገሥጽ፥**
**እንደ ብር የተፈተኑት አሕዛብ እንዳይዘጉ**
**ሰልፍን የሚወድዱትን አሕዛብን በትናቸው።**
[31]**መኳንንት ከግብጽ ይመጣሉ**
**ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች።**

**68፡28-31** ይህ አንጓ በመጠኑ የሚዛመደው ያህዌ ግብፅን ድል ከማድረጉ ጋር ነው። እሱም በዘጸአት ወይም ኋላ ላይ ወታደራዊ ወረራ መሆኑ ርግጠኝነት የለውም።

ሆኖም፣ በማሸነፉ አስደናቂ ስጦታ ያህዌን ለማምለክ ወደ ኢየሩሳሌም መጥተዋል (ዝኪ. ቁ. 31፤ ኢሳ. 19:19-22፤ 45:14)። ይህ ሁለንተናዊ አጽንዖት ነው (ዝኪ. ቁ. 32-35) መዝሙር 65-68ን የሚያያይዘው።

**68፡28** ኃይል/ብርታት (ቢዲቢ 738) የእግዚአብሔር ነው፣ እሱም ለሕዝቡ ብሎ ተግባራዊ አደረገው፣ አሕዛብን ወደ እርሱ ለመማረክ።

**68:29**
**አአመመቅ፣ አኪጀት ፣**
**አየተመት** **“ምክንያቱም”**
**አእቅ፣ አኢመቅ፣**
**ጀፒኤስአኤ** **“ከ”**
**LXX** **“በውጤቱም”**
**አእት መጽሐፍ ቅዱስ** **“ስትወጣ”**

ኤምቲ መስተጻምር አለው፣ እሱንም በብዙ መንገዶች መረዳት የሚቻል። እሱም ከቁጥር 1 የሚጠቅስ ይመስላል፣ እዚያም ያህዌ ለድርጊት ሲነሣ፣ በእስራኤል ወገን ለጦርነት።

**68፡30** ***“ገሥጽ”*** ይህ *ቃል* ተተኳሪ (ቢዲቢ 172፣ ኬቢ 199)። ይህ ቃል ጥቅም ላይ የዋለው እግዚአብሔር በአሕዛብ ላይ መፍረዱን ነው መዝ. 9:5፤ ኢሳ. 17:13። እዚህ ጥቅም ላይ የዋለው ለግብፅ ይመስላል (ሕዝ. 29:3፤ 32:2፤ ኢሳ. 27:1 ይሆናል)። እሷና ወደ ደቡብ ሲል ያሉት አሕዛብ (ማለትም፣ ኢትዮጵያ/ኩሽ) ሁለቱም ተለይተው ተጠርተዋል፣ ቁጥር 31 ላይ።

አእቅ መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 934) እሱን የሚተረጉመው “የጦርነት ጩኸት” በሚል ነው።

▣
**አአመመቅ፣ አየተመት** **“በእግር መደፍጠጥ”**
**አኪጀት** ***“ሁሉም እስከሚገዛ ድረስ”***
**አእቅ** **“ሁሉም እስከሚሰግዱ ድረስ”**
**አኢመቅ** **“የሚሰግዱ”**
**ጀፒኤስአኤ** **“እስከሚገዙ ድረስ”**

ኤምቲ "መደፍጠጥ" "መርገጥ" "በእግር በመደፍጠጥ/በመርገጥ ማበላሸት" የሚል አለው (ቢዲቢ 952፣ ኬቢ 1279፣ ምሳ. 25:26)። ተመሳሳይ ሥር (በተተኳሪ መልኩ" ፍችው "ራስን ዝቅ ማድረግ" ነው። ሁለቱም ፍችዎች ሕዝ. 32፡2 ወይም 34፡18 ይጠቅሳሉ፣ እሲያም ተመሳሳይ ግሥ ለግብፅ መዋረድ ጥቅም ላይ የዋለበት።

▣ **"የብር ድቃቂ"** በድጋሚ ያልተለመዱ ቃላት ወይም ጽሑፋዊ ብልሽቶች የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ርግጠኛ እንዳይሆኑ አድርገዋቸዋል።

"ድቃቂ፣" የሚለው ቃል ሃገ ፣ ይኸውም ቢዲቢ የሚለው "ቁራጭ" ወይም "አራት ማዕዘን" ፍች ይኖረዋል)።

እሱን ወደ ኀጿבּ ማሻሻል ይቻላል (ቢዲቢ 131 I)፣ ፍችውም "የከበረ ደንጊያ" (ኢዮብ 22:24፣ NIDOTTE፣ ቅጽ. 1፣ ገጽ. 699-700)፣ "ወርቅ" ይሆናል። እንደዚያ ከሆነ፣ እንግዲያውስ የስንኙ ቅኔ ትርጓሜ (ቁ. 30ሐ) ሊሆን የሚችለው "ከወርቅና ከብር ጋር መስገድ" ነው (ማለትም፣ ለያህዌ ስጦታ)።

**68:31**

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**

| | |
|---|---|
| **የተእመቅ፣ LXX** | ***"መኳንንት ከግብፅ ይመጣሉ"*** |
| **አየተመት** | ***"ነሐስ ከግብፅ ይመጣል"*** |
| **አእቅ** | ***"ሹማምንት ከግብፅ ይመጣሉ"*** |
| **አኢመቅ** | ***"መኳንንት ከግብፅ ይመጣሉ"*** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | ***"ስጦታ የያዙ ከግብፅ ይመጣሉ"*** |

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 297) "የነሐስ ቁሳቁስ" (ቢዲቢ 365) "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ)። እሱም እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ። ሌሎቹ ትርጉሞች የሚከተሉት ጥንታዊዎቹን ቅጅዎችንና ራቢያዊ ትንታኔዎችን ነው።

ቁ. 30ሐ እና ቁ. 31ሀ፣ለን መመልከት ይቻላል፣ ወደ እግዚአብሔር እንደመጣ ስጦታ፣ በሰሜን አፍሪካ ሕዝቦች (ጄፒኤስኦኤ)።

1. ወርቅ
2. ብር
3. ነሐስ

▣ **"እጆችዋን በፍጥነት ትዘረጋለች"** ይህ የፊተኛውን ማስታወሻ ከመረዳት ጋር ይገጥማል። "መሮጥ" የሚለውን ግሥ ማሻሻል አስፈላጊ አይደለም (ቢዲቢ 930፣ ኬቢ 1207፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*) ወደ "መዘርጋት" (አእመቅ) ኤምቲ የተመሳሳዩ እውነታ ፈሊጥ ስለሆነ።

## *መዝሙር ፡ 68፡32-35*

**32የምድር ነገሥታት፥ ለእግዚአብሔር ተቀኙ፥**
**ለጌታም ዘምሩ። ሴላህ።**
**33በምሥራቅ በኩል ወደ ሰማየ ሰማያት ለወጣ ለእግዚአብሔር ዘምሩ**
**የኃይል ቃል የሆነ ቃሉን፥ እነሆ፥ ይሰጣል።**
**34ለእግዚአብሔር ክብርን ስጡ**
**ግርማው በእስራኤል ላይ፥**
**ኃይሉም በደመናት ላይ ነው።**
**35እግዚአብሔር በቅዱሳኑ ላይ ድንቅ ነው**
**የእስራኤል አምላክ እርሱ ኃይልን ብርታትንም ለሕዝቡ ይሰጣል**
**እግዚአብሔርም ይመስገን።**

**68፡32-35** ይህ አንጓ የሚያጠናክረው የያህዌን ሁለንተናዊ አምልኮ ነው፣ በኢየሩሳሌም፣ ቁጥር 31 ላይ የተጠቀሰው።

ተተኳሪዎቹን ተገንዘብ።

1. ለእግዚአብሔር ዘምሩ – ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. ለጌታም ምስጋና ዘምሩ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ *ፔል ተተኳሪ*
3. ኃይልን ለእግዚአብሔር ስጡ – ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 29:1-2፤ 1 ዜና. 16:28-29

ያህዌ የተገለጸው፣ እንደ

1. በብሩኅ ሰማያት ላይ ለወጣ (ማለትም፣ በነጎድጓማ ደመናት)
2. እሱም ፊት ለፊት በብርቱ ድምጽ ይናገራል (ማለትም፣ መብረቅ፣ ኢሳ. 30:30፤ ራዕ. 11:19፤ 14:2፤ 16:17-18)
3. ክብሩ በእስራኤል ላይ ነው
4. ብርታቱ በሰማያት ላይ ነው
5. ከመቅደሱ ድንቅ ነው
6. ለሕዝቡ ብርታትና ኃይል ይሰጣል
7. በእነርሱም እግዚአብሔር ይመሰገናል

**68፡33ሀ** ምስያው ወደ ኋላ ተመልሶ ወደ ዘዳ. 33፡26 እና መዝ. 18፡10 ይጠቅሳል፣ ደግሞም ቁ. 4ለ ተመልከት።

"ሰማየ ሰማያት" የምድርን ደመናት ይገልጻል (ዝኪ. ቁ. 34ሐ)፣ የእግዚአብሔርን መኖርያ ሳይሆን።

የእርሱ ብርቱ ድምጽ የፍጥረት ጠቃሽ ነው፣ በንግግር ቃል ዘፍጥረት 1 ላይ።

**69፡35 "ድንቅ"** ይህ ገለጻ ተመልሶ ወደ ዘዳ. 7:21፤ 10:17 ይሄዳል፣ ደግሞም መዝ. 47:2 እና 66:5 ማስታወሻ ተመልከት። እሱም የሚያመለክተው የያህዌን የተቀደሰ ባሕርይ ነው፣ እንዲሁም የኪዳን ማዳኑን ድርጊቶች።

▣ **"ለሕዝቡ ብርታትና ኃይል ይሰጣል"** ይህ ሌለኛው ጠቃሽ ሊሆን ይችላል

1. ዘጸአት
2. የምድረ በዳ መንከራተት
3. የከነአን ድል
4. የእርሱ ቀጣይነት ያለው መገኘት፣ ከእስራኤል ጋር

# መዝሙር 69
# የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የመከራ ጩኸትና በጠላቶች ላይ ውግዘት<br>ኤምቲ መግቢያ ለመዘምራን አለቃ፤ በበገናዎች። ስለ ሾሻኒም የዳዊት መዝሙር። | አስቸኳይ የዕርዳታ ጸሎት በችግር ጊዜ | የመታደግ ጸሎት ከግል ጠላቶች | የርዳታ ጩኸት | ሰቆቃ |
| 69:1-4 | | | | |
| | 69:1-3 | 69:1-3 | 69:1-3 | 69:1 |
| | | | | 69:2 |
| | | | | 69:3 |
| | 69:4 | 69:4 | 69:4 | 68:4 |
| 69:5-12 | | | | |
| | 69:5-12 | 69:5 | 69:5-8 | 69:5 |
| | | 69:6-8 | | 69:6ሀ፣ለ |
| | | | | 69:6ሐ፣መ |
| | | | | 69:7-9 |
| | | 69:9-12 | 69:9-12 | |
| | | | | 69:10-12 |
| 69:13-15 | | | | |
| | 69:13-15 | 69:13-15 | 69:13-15 | 69:13 |
| | | | | 69:14-15 |
| 69:16-19 | | | | |
| | 69:16-18 | 69:16-18 | 69:16-18 | 69:16-18 |
| | 69:19-21 | 69:19-21 | 69:19-21 | 69:19-20 |
| 69:20-21 | | | | |
| | | | | 69:21-23 |
| 69:22-28 | | | | |
| | 69:22-28 | 69:22-29 | 69:22-28 | |
| | | | | 69:24-26 |
| 69:29-33 | | | | |
| | 69:29-33 | | 69:29-33 | |
| | | | | 69:27-28 |
| | | | | 69:29-31 |
| | | 69:30-33 | | |
| | | | | 69:32-34 |
| 69:34-36 | | | | |
| | 69:34-36 | 69:34-36 | 69:34-36 | |
| | | | | 69:35-36 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙሩ እጅግ የተዘወተሩ የአምላክ ስሞችን ይጠቀማል።

1. ኤሎሂም (ማለትም፣ በመለኮት ፈጣሪነት፣ ደጋፊነት፣ እና ሰጪነት ላይ ያተኮረ መጠሪያ፣ በዚህ ዓለም ላይ ላለ ሕይወት ሁሉ) – ቁ. 1፣6፣13፣29፣30፣32፣35 (ደግሞም የተለየ መልክ ቁ. 3 ላይ፣ "አምላክ" [*ኤሎሀ*] እና ቁ. 6፣ "አምላክ" [*ኤሎሀ*] የእስራኤል")
2. ያህዌ (ማለትም፣ በመለኮት አዳኝነት፣ ተቤዠነት፣ ኪዳን መሥራች አምላክነት ላይ ያተኮረ መጠሪያ)
   ሀ. የሠራዊት ጌታ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1:1 ላይ)፣ ቁ. 6
   ለ. ያህዌ፣ ቁ. 13፣16፣31፣33

ለ. መዝሙረኛው ከሕይወት፣ ከቤተሰብ፣ እና ከወዳጆች እንደተገለለ ይሰማዋል (ዝከ. ቁ. 8) በእግዚአብሔር ላይ ባለው እምነት (ዝከ. ቁ. 9)።

ኢየሱስ ይሄንን መዝሙር ተጠቅሟል፣ የገዛ ራሱን የመገለል ስሜት ለመግለጽ፣ በወገኖቹ በአይሁድ። ልዩነቱ መዝሙረኛው በቀልና ፍርድን ሲሻ (መዝ. 69፡22-28)፣ ኢየሱስ ግን መከራን ለሚያሳዩት ምሕረትን ይለምናል፣ በአላዋቂነታቸው ላይ በመመሥረት (ሉቃስ 23፡34)።

ሐ. ይህ መዝሙር ብዙ ጸሎቶች አሉት፣ አንዳንዶቹ በተተኳሪነት ሲገለጹ እንዲሁም አንዳንዶቹ ባልተጠናቀቁ ተገልጸዋል፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ (ቁጥር 6 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 69፡1-4**

**[1]አቤቱ፥ ውኃ እስከ ነፍሴ ደርሶብኛልና**
**አድነኝ።**
**[2]በጥልቅ ረግረግ ጠለቅሁ መቋሚያም የለኝም።**
**ወደ ጥልቅ ባሕር ገባሁ ማዕበልም አሰጠመኝ።**
**[3]በጩኸት ደከምሁ ጕሮሮዬም ሰለለ**
**አምላኬን ስጠብቅ ዓይኖቼ ፈዘዙ።**
**[4]በከንቱ የሚጠሉኝ ከራሴ ጠጕር በዙ**
**በዓመፅ ያሚያሳድዱኝ ጠላቶቼ በረቱ**
**በዚያን ጊዜ ያልቀማሁትን መለስሁ።**

**69፡1-4** ይህ አንዳ የመታደግ ጸሎት ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 446፣ ኬቢ. 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*) በርካታ የመከራ ዘይቤዎችን ተጠቅሟል።
1. ውኃ እስከ ነፍሴ ደርሶብኛልና (ዝከ. ቁ. 2ለ፤ መዝ. 32:6)
2. በጥልቅ ረግረግ ጠለቅሁ (መዝ. 40:2)
3. መቋሚያም የለኝም (ቢ.ዲ.ቢ. 765፣ እዚህጋ ብቻ ብኪ. ላይ፣ ከግርማ ጋር ተመሳሳይ የሆነ መዝ. 40፡2)

እሱም ይሄንን ጸሎት ቁጥር 14-15 ላይ ይደግመዋል። አይሁድ ከፊል ደረቅማ በሆነ ቦታ ነው የሚኖሩት፣ እናም ውኃ ይፈራሉ። ሰሎሞንም እንኳ ቢሆን ባሕረኞቹ እንዲሆኑ ያደረገው ፍንቂያውያንን ነው እንጂ አይሁድን አይደለም። ፍልስጥኤም እጅግ በከፋ አደገኛ ጎርፍ የታወቀ ነው፣ በክረምት ወራት።

**69፡1 "ነፍስ"** ይህ በጥሬው *ኔፊሽ* ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 659)። መዝ. 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት። እዚህ የሚጠቅሰው "አንገት፣" ነው፣ እንደዚያ ከሆነ ግን፣ ይህ ያልተለመደ ነው (ዮናስ 2፡5ን ማየት ይቻላል)።

**69፡2-3** የምናቡ ተለዋዋጭነት በተቃርኖው ሊታይ ይችላል፣ በብዙ ውኃ ቁጥር 2 ላይ እና በደረቀ ጕሮሮ ቁጥር 3 መካከል (ቢ.ዲ.ቢ. 359፣ ቃሉ እዚህጋ ብቻ ነው፣ ብኪ. ላይ፣ ኒዶቴ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 295)። ውኃ ብርቱ ተምሳሌት ነው።
1. የፍጥረት ውኃዎች
2. ጎርፍ
3. አስፈላጊው ዓመታዊ ዝናብ
4. እንባ
5. ለሕይወትና ለጤና አስፈላጊ

**69፡3-4** ቁጥር 3 ዘይቤአዊ ቋንቋ ነው፣ ኀዘንንና ልቅሶን የሚገልጽ፣ መዝሙረኛው ራሱን ባገኘበት ሁኔታ ውስጥ (ዝከ. ቁ. 10-11)። ያ ሁኔታ ቁጥር 4 ላይ ተገልጿል።
1. ብዙ ሰዎች (ማለትም፣ የራሱ ሰዎች) ያለ ምክንያት ጠሉት (ዮሐንስ 15፡25)
2. እነርሱም ሊያጠፉት/ሊገድሉት ፈለጉ
3. እነርሱ ብርቱ ሰዎች ናቸው (ዝከ. ቁ. 12)

መዝሙረኛው የሚያስረግጠው የእነርሱ ጥላቻና ጥቃት ያለምክንያት ነው (ዝከ. ቁ. 4ሐ)። እሱም ይሄንን ንጽሕናውን እንደ ማሳያ መንገድ ተጠቅሞበታል፣ በሁሉም አካባቢ፣ ከሙሴ ኪዳን ጋር በተያያዘ። እሱ ኃጢአት-የለሽ እንደሆነ አይገልጽም (ዝከ. ቁ. 5)። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 18፡20-24 ላይ።

**መዝሙር ፡ 69፡5-12**

**[5]አቤቱ፥ አንተ ስንፍናዬን ታውቃለህ፥**
**ኃጢአቴም ከአንተ አልተሰወረም።**
**[6]አቤቱ የሠራዊት አምላክ፥ ተስፋ የሚያደርጉህ በእኔ አይፈሩ**
**የእስራኤል አምላክ ሆይ፥ የሚሹህ በእኔ አይነወሩ።**
**[7]ስለ አንተ ስድብን ታግሻለሁና፥**
**እፍረትም ፊቴን ሸፍናለችና።**
**[8]ለወንድሞቼ እንደ ሌላ፥**
**ለእናቴ ልጆችም እንደ እንግዳ ሆንሁባቸው፥**
**[9]የቤትህ ቅንዓት በልታኛለችና፥**
**የሚሰድቡህም ስድብ በላዬ ወድቆአልና።**
**[10]ነፍሴን በጾም አስመረርሁአት፥**
**ለስድብም ሆነብኝ።**
**[11]ማቅ ለበስሁ**
**ምሳሌም ሆንሁላቸው።**
**[12]በደጅ የሚቀመጡ በእኔ ይጫወታሉ**
**ወይን የሚጠጡ እኔን ይዘፍናሉ።**

**69፡5-12** ይህ አንጓ የሚገልጸው የሁሉንም አማኞች ሁኔታ ነው። ኃጢአተኛ መሆናችንን እናውቃለን (ቁ. 5) ነገር ግን መልካምን ሕይወት ለመኖር እንሻለን (ዝከ. ቁ. 9ሀ)። ከዚህ ተቃርኖ አኳያ መዝሙረኛው በርካታ ጥያቄዎች አሉት።

1. አንተን ተስፋ የሚያደርጉህ (ማለትም፣ የሚታመኑህ) በእኔ ምክንያት አይፈሩ
2. አንተን የሚሹህ በእኔ ምክንያት አይነወሩ

ይህ መዝሙረኛ በግልጽ የሚያስረግጠው የእርሱ ችግር የተፈጠረው በያህዌ ላይ ባለው እምነት መሆኑን ነው (ዝከ. ቁ. 7፣9)። ይህም የመዝሙሩ ገጽታ ነው የኢየሱስ ፍጹም ጠቃሽ ያደረገው (ዮሐንስ 2፡17)። ደግሞም ጳውሎስ ሮሜ. 15፡3 ላይ ተቀያሪ ገጽታ አክሎበታል (ኢሳይያስ 53፤ ማርቆስ 10፡45) ለኢየሱስ ቁ. 9ለ ላይ።

**69፡5 "ኃጢአቴም ከአንተ አልተሰወረም"** መዝ. 44፡21 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

**69፡6 "አይ..."** ይህ የመጀመሪያው ነው፣ ከተለጣጣቂዎቹ ያልተጠናቀቁት፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉት። ይህ መዝሙር በርካታ የዚህ ዓይነቶች አሉት።

1. አይፈሩ...፣ ቁ. 6 – ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
2. አይነወሩ...፣ ቁ. 6 – ቢዲቢ 483፣ ኬቢ 480፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ
3. አይሸፍነኝ...፣ ቁ. 15 – ቢዲቢ 1009፣ ኬቢ 1474፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
4. አይዋጠኝ፣ ቁ. 15 – ቢዲቢ 118፣ ኬቢ 134፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
5. በእኔ ላይ አፉን አይዝጋ...፣ ቁ. 15 – ቢዲቢ 32፣ ኬቢ 37፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
6. ማዕዳቸው... ማሰናከያ ይሁንባቸው፣ ቁ. 22a – ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ *ቃል* ተጽዕኗዊ
7. ወጥመድ ይሁንባቸው፣ ቁ. 22ለ – ከቁ.6 እንደሆነ ይታሰባል
8. ዓይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ፣ ቁ. 23 – ቢዲቢ 364፣ ኬቢ 361፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
9. መዓትህን በላያቸው አፍስስ፣ ቁ. 23 – ቢዲቢ 673፣ ኬቢ 727፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ
10. ማደሪያቸው በረሀ ትሁን፣ ቁ. 25 – ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ *ቃል* ተጽዕኗዊ
11. በድንኳኖቻቸው የሚቀመጥ አይገኝ፣ ቁ. 25፣ – ከቁ. 10 ጋር ተመሳሳይ
12. በጽድቅህም አይግቡ፣ ቁ. 27 – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
13. ከሕያዋን መጽሐፍ ይደምሰሱ፣ ቁ. 28 – ቢዲቢ 562፣ ኬቢ567፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ
14. ከጻድቃንም ጋር አይጻፉ፣ ቁ. 28 – ቢዲቢ 507፣ ኬቢ 503፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ
15. የፊትህ መድኃኒት ይቀበለኝ፣ ቁ. 29 – ቢዲቢ 960፣ ኬቢ 1305፣ *ፒል* ያልተጠናቀቀ (በአዎንታዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ)
16. ሰማይና ምድር ያመሰግኑታል፣ ቁ. 34 – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ *ፒል* ያልተጠናቀቀ (በአዎንታዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ)

እነዚህ ሁሉ (ከቁ. 15 እና 16 በቀር) የመዝሙረኛውን ጸሎት የሚገልጹ ናቸው፣ ለእግዚአብሔር፣ በጠላቶቹ ላይ እንዲነሣ። ይኼኛው የመዝሙሩ አካል ነው፣ ከኢየሱስ የዚህ መዝሙር አጠቃቀም ላይ የሌለው፣ በመስቀል ላይ።

**69፡10-11** የመዝሙረኛው የጸሎት ድርጊቱ እና ራሱን ዝቅ ማድረጉ "መሳለቂያ" (ቢዲቢ 357)፣ "መዘበቻ" (ቢዲቢ 605) ሆነበት ፣ ለብርቱ ጠላቶቹ (ማለትም፣ "በደጅ የሚቀመጡ፣" ቁ. 12ሀ)፣ እንዲሁም የወይን ጠጅ ለሚጠጡ (ቁ. 12ለ)።

▣ **"መጾም... ማቅ መልበስ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የኀዘን ሥርዓት፣ መዝ. 30፡11 ላይ።

ቁጥር 3-12 ሰዎች መካከል ያለውን ተቃርኖ ተገንዘብ።

1. እግዚአብሔርን የሚፈራው እና የሚያገለግለው ጸሐፊ በጸሎት፣ በጾም፣ እና በአገልግሎት

2. የማይፈሩት በደጅ ላይ (ማለትም፣ የአመራር ስፍራ) እነርሱም የእርሱን መሰጠት የሚያንኳስሱ፣ የሰካርም ዘፈን የሚዘፍኑ

**መዝሙር ፡ 69፡13-15**

[13]**አቤቱ፥ በመልካሙ ጊዜ ጸሎቴ ወደ አንተ ነው አቤቱ፥**
**በምሕረትህ ብዛት በማዳንህም**
**እውነት አድምጠኝ።**
[14]**እንዳይውጠኝ ከረግረግ አውጣኝ**
**ከሚጠሉኝና ከጥልቅ ውኃ አስጥለኝ።**
[15]**የውኃው ማዕበል አያስጥመኝ፥**
**ጥልቁም አይዋጠኝ፥**
**ጕድጓድም አፉን በእኔ ላይ አይዝጋ።**

**69፡13-15** *መዝሙረኛው ጸሎቱን ቀጥሏል። የሚገለጸውም*

1. *ለያህዌ*
2. በምቹ ሰዓት

*መዝሙረኛው* በያህዌ ላይ ያለው *መታመን*፣ በችግር ጊዜ መሐል እንኳ ሆኖ፣ እንዲሁም በተገቢው ሰዓት እንደሚመልስለትና እንደሚያድነው ማወቁን ተገንዘብ (መዝ. 32:6፤ ኢሳ. 49:8፤ 2 ቆሮ. 6:2)። ሁነኛ ሰዓት አለ (መክ. 3፡1-8)።

*መዝሙረኛው ይታመናል*፣ በያህዌ

1. ቸርነት (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 5፡7 ላይ)፣ ቁ. 13ለ
2. *ታማኝነት* (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 12፡1 ላይ)፣ ቁ. 13ሐ

ሁለቱን ተተኳሪዎች ተገንዘብ።

1. አድምጠኝ – ቢዲቢ 722፣ ኬቢ 851፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ ቁ. 13ሐ
2. አድነኝ – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ ቁ. 14ሀ

ቁጥር 14-15 የሚገልጸው መዝሙረኛው ከምን እንዲድን መፈለጉን ነው።

1. እንድሰጥም አትተወኝ (ዝከ. ቁ. 1-2)። የተለያየ የቃላት አደራደር አለ
   ሀ. *የትንታኔ ቁልፍ ለብሊ፣* በጀን አውንስ፣ እዚያም እንደ ቃል ተተኳሪ የሚገለጽበት (ገጽ 374)
   ለ. *የብሊ የቃላት ኢደራደር መመሪያ፣* በቢኦል፣ ባንክስ እና ስሚዝ፣ እሱን የሚገልጸው እንደ ቃል ተጓዳኝ ነው (ገጽ 439)
2. ከ... እድን ዘንድ። የተለያየ የቃላት አደራደር አለ
   ሀ. *የትንታኔ ቁልፍ – ኒፋል* ያልተጠናቀቀ(ገጽ 374)
   ለ. *የቃላት ኢደራደር መመሪያ – ኒፋል* ተጓዳኝ (ገጽ 439)

*መዝሙረኛው* ተቃዋሚዎቹን እንደ "ጠላቶቹ" እና "ጥልቅ ውኃ" አድርጎ ይገልጻቸዋል። (ቁ. 14ለ)። ቁጥር 14 እና 15 ተመሳሳይ ምስያ ይጠቀማሉ፣ እንደ ቁ. 1-2 (መዝ. 124:4-5፤ ኢሳ. 43:2)።

**69፡15ሐ "ጥልቅ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት: ሙታን የት ናቸው? መዝ. 1፡6 ላይ፣ በተለይም ሲኦል፣ የሙታን ማቆያ ስፍራ፣ እሱም ዘወትር "ከጥልቁ" ጋር ትይዩ የሆነ (ዘኁ. 16:33፤መዝ. 28:1፤ 88:3-4፤ ምሳ. 1:12)። እሱም የሚጠቅሰው መቃብርን ነው (መዝ. 141:7)።

**መዝሙር ፡ 69፡16-19**

[16]**አቤቱ፥ ምሕረትህ መልካም ናትና ስማኝ።**
**እንደ ርኅራኄህም ብዛት ወደ እኔ ተመልከት**
[17]**ከባሪያህም ፊትህን አትሰውር**
**ተጨንቄአለሁና ፈጥነህ አድምጠኝ።**
[18]**ነፍሴን ተመልከተህ ተቤዣት**
**ስለ ጠላቶቼም አድነኝ።**
[19]**አንተ ስድቤን እፍረቴንም ነውሬንም ታውቃለህ**
**የሚያስጨንቁኝ ሁሉ በፊትህ ናቸው።**

**69፡16-19** ይህ *አንጓ* ባሕርይ ያደረገው የልባዊ ጸሎት ተተኳሪዎችን ነው።

1. አድምጠኝ፣ ቁ. 16 – ቢዲቢ 772 I፣ ኬቢ 851፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. ወደ እኔ ተመልከት፣ ቁ. 16 – ቢዲቢ 815፣ ኬቢ 937፣ *ቃል ተተኳሪ* (መዝ. 27:9፤ 102:2፤ 143:7)
3. ፍጠን (ቸኩል)፣ ቁ. 17 – ቢዲቢ 554፣ ኬቢ 553፣ *ፒል ተተኳሪ*
4. አድምጠኝ፣ ቁ. 17 – እንደ ቁ. 1 ተመሳሳይ
5. ወደ እኔ ቅረብ፣ ቁ. 18 – ቢዲቢ 897፣ ኬቢ 1132፣ *ቃል ተተኳሪ*
6. ተቤዠኝ፣ ቁ. 18 – ቢዲቢ 145 I፣ ኬቢ 165፣ *ቃል ተተኳሪ*
7. ተዋጀኝ፣ . 18 – ቢዲቢ 804፣ ኬቢ 911፣ *ቃል ተተኳሪ* (ልዩ ርዕስ ተመልከት: *መዋጀት/መቤዠት* መዝ. 19፡14 ላይ)

የዚህን የጸሎት ጥያቄዎች መሠረቶች ተገንዘብ፡

1. የያህዌ ቸርነት (ቢዲቢ 338) መልካም ነው፣ ቁ. 16
2. የያህዌ ታላቅ ርኅራኄ ("ምሕረት፣" ቢዲቢ 933)፣ ቁ. 16
3. ያህዌ የመዝሙረኛውን ሁኔታ ያውቃል፣ ቁ. 19

ሀ. የመዝሙረኛው ልብ
ለ. የሚያስጨንቁት ልቦች

**69፡17 "ባሪያህ"** ይህ ሊሆን የሚችለው
1. የተለየ መሪ፣ እንደ ሙሴ፣ ኢያሱ
2. ዳዊትን ወይም የእርሱን ንጉሣዊ ዝርያ የሚጠቅስ (ማለትም፣ በመዳረሻው መሲሕ)
3. የመሲሐዊው ግጥሞች፣ የኢሳይያስ 40-55 የተለየ አገልጋይ
4. የኪዳን አማኝ የተለመደ መጠሪያ (ዝከ. ቁ. 36)

**69፡19** አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ቁ. 19ን የሚመለከቱት ከቁ. 20-21 ጋር እንደሚሄድ ነው።
የምስራቃዊውን የሕይወት አተያይ ተገንዘቡ፣ እሱም ለአንዱ መልካም ስም አጽንዖት የሚሰጥ።
1. መሳለቅ – ቢዲቢ 357፣ ዝከ. ቁ. 20
2. ኀፍረት – ቢዲቢ 102
3. ውርደት – ቢዲቢ 484

**መዝሙር ፡ 69፡20-21**

**20 ነፍሴ ስድብንና ኃሣርን ታገሠች**
**አስተዛዛኝም ተመኘሁ አላገኘሁም።**
**የሚያጽናናኝም አጣሁ።**
**21 ለመብሌ ሐሞት ሰጡኝ፥**
**ለጥማቴም ሆምጣጤ አጠጡኝ።**

**69፡20-21** የዕብራይስጡ ቃል "ሐሞት" (ቁ. 21) "መርዝ" ነው (ቢዲቢ 912 II)፣ ነገር ግን የተበላሸ ወይንን ሊያመለክት ይችላል (ዘዳ. 32፡32)። LXX ነው ወደ "ሐሞት" ወይም "መራራ" የቀየረው (አረንጓዴ — ቾሊ)። ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ "መርዝ" እና "ሆምጣጤ" የሚያመለክቱት የመዝሙረኛውን ጠላቶች ስድብ ነው (ማለትም፣ የኪዳን ተካፋዮች፣ የቅርብ ጓደኞች፣ እና ቤተሰብ፣ ዝከ. ቁ. 8)።

ይህ አንጓ ማቴ. 27፡34 ላይ ተጠቅሷል፣ በኢየሱስ መሰቀል የተፈጸመ። ቁጥር 21ለ ማርቆስ 15:23፤ ሉቃስ 23:36፤ ዮሐንስ 19:28-30 ላይ ተጠቅሷል። ይህ መዝሙርና መዝሙር 22 ሁለቱ የብኪ ጠቃሾች እና ጥቅሶች ናቸው፣ ለኢየሱስ የመስቀል ሥራ በአኪ ጥቅም ላይ የዋሉ።

እነዚህ መዝሙራት ትንበያዊ አይደሉም፣ ዐቢይ ምድባዊ እንጂ። መዝሙር 22 ላይ ማስታወሻ ተመልከት። ቁጥር 22-28 ከኢየሱስ አቋም ወይም ከመስቀል ቃሎቹ ጋር የሚገጥሙ አይደሉም።

**69፡20 "እጅግ ታምሜአለሁ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 633፣ ኬቢ 683) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ። ቢዲቢ የሚለው "መታመም" ነው፣ ኬቢ ግን የሚለው "የማይድን" ነው፤ አኢመቅ "ከፈውስ የራቀ" ይለዋል። ፍችው ሊሆን የሚችለው "ተስፋ መቁረጥ" ነው (አየተመት፣ አእቅ፣ ጀፒኤስአኤ)። "መታመም" ከሆነ፣ እንግዲያውስ ቁ. 29 ትይዩ ነው።

**69፡21 "ሆምጣጤ"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 330) የሚያመለክተው ርካሽ ወይን ነው (ዘኁ. 6፡3)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አልኮልና አልኮለኝነት መዝ. 4፡7 ላይ።

**መዝሙር ፡ 69፡22-28**

**22 ማዕዳቸው በፊታቸው ለወጥመድ**
**ለፍዳ ለዕንቅፋት ትሁንባቸው**
**23 ዓይኖቻቸው እንዳያዩ ይጨልሙ፥**
**ጀርባቸውም ዘወትር ይጕበጥ።**
**24 መዓትህን በላያቸው አፍስስ፥**
**የቍጣህ መቅሠፍትም ያግኛቸው።**
**25 ማደሪያቸው በረሃ ትሁን፥**
**በድንኳኖቻቸውም የሚቀመጥ አይገኝ**
**26 አንተ የቀሠፍኸውን እነርሱ አሳድደዋልና፥**
**በቍስሌም ላይ ጥዝጣዜ ጨመሩብኝ።**
**27 በኃጢአታቸው ላይ ኃጢአትን ጨምርባቸው፥**
**በጽድቅህም አይግቡ።**
**28 ከሕያዋን መጽሐፍ ይደምሰሱ፥**
**ከጻድቃንም ጋር አይጻፉ።**

**69፡22-28** ይህ አንጓ የሚገልጸው መዝሙረኛው ያህዌን የሚጠይቀውን ነው፣ በጠላቶቹ ላይ እንዲያደርግ ያለውን። ቁ. 6 ላይ ያሉትን ማስታወሻዎች ተመልከት (በተጽዕኗዊ ጥቅም ላይ የዋሉ ያልተጠናቀቁዎች)። እነርሱም
1. ሦስት ተጽዕኗዊዎች
2. አምስት ያልተጠናቀቁዎች፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ
3. ሁለት ተተኳሪዎች

ሀ. ጀርባቸውንም ዘወትር አጉብጥ – ቢ.ዲ.ቢ. 588፤ ኬ.ቢ. 609፤ *ሂፊል ተተኳሪ* (ይህ የቁ. 29ለ ቅኔአዊ ተቃራኒ ነው)
ለ. መዓትህን በላያቸው አፍስስ – ቢ.ዲ.ቢ. 1049፤ ኬ.ቢ. 1629፤ *ቃል ተተኳሪ*

**69፡22** ይህ ቁጥር ሮሜ 11፡9-10 ላይ ተጠቅሷል፣ እርሱም የማያምነውን እስራኤል የሚመለከት።
ቁጥር 25 ሐዋ. 1፡20 ላይ ተጠቅሷል፣ ስለ "ደም መሬት" በካህናት የተገዛ፣ በይሁዳ የከህደት ገንዘብ።
ቁጥር 27ሀ ሮሜ 1፡28 ላይ የተጠቀሰው ይሆናል፣ እሱም የሰው ልጆች ሁሉ ኃጢአተኛ መሆናቸውን የሚጠቅስ (ሮሜ. 3፡9-18፣ 23)።

◘

**አአመመቅ** **"በሰላም በሆኑበት ጊዜ"**
**አኪጀት** **"በደኅንነታቸው"**
**አእቅ** **"የተቀደሱ በዓላት"**
**አኢመቅ** **"በበረከታቸው"**
**የተእመቅ** **"በደኅንነት እንደሆኑ ሲሰማቸው"**

ኤምቲ "ደኅንነት" አለው (ቢ.ዲ.ቢ. 1022) የዓረብኛ ታርጉምስ ግን "መሥዋዕታዊ በዓላት" የሚል አለው (አየተመት፣ አእቅ)። አየተመት ወደ "ለወዳጅነታቸው ወጥመድ" ወደሚል ይቀይረዋል፣ (ጄፒኤስኦኤ) ከመዝ. 55፡20 ላይ ፈሊጥ በመውሰድ (ማለትም፣ የቅርብ ወዳጆች)።

**69፡25** ይህ ከምድረ-በዳ መንከራተት ጊዜ የሆነ ምናብ ነው።

**69፡26** ይህ ቁጥር የሚያንጸባርቀው ኢሳ. 53፡4 እና 10 (ዝኪ. 2 ቆሮ. 5፡21ን ነው)።
የግሥ መልክ (ቢ.ዲ.ቢ. 319) የስሙ ትርጉም "የቆሰለ" የሚለው ኢሳ. 53፡5 ላይ ነው የሚከሰተው (ቢ.ዲ.ቢ. 319፤ ኬ.ቢ. 320፤ *ፖኣል* አንቀጽ)። ግሡ "የተመታ" የሚለው (ቢ.ዲ.ቢ. 645፤ ኬ.ቢ. 697፤ *ሆፋል* አንቀጽ) ደግሞ ኢሳ. 53፡4 ላይ ይከሰታል።
ቁጥር 21 እና 26 በርግጠኝነት የወንጌል ጸሐፊዎች ግንኙነቱን እንዲያዩ ምክንያት ሆኗቸዋል!

**69፡28** በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) የዜጎች ከተሞች ስሞች በጥቅሉ ላይ ይመዘገብ ነበር። መጽሐፍ ቅዱስም ይሄንን ምስያ ይጠቀማል፣ የእግዚአብሔርን እውቀት ለማንጸባረቅ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሁለቱ መጻሕፍት መዝ. 9፡5 ላይ።

## መዝሙር ፡ 69፡29-33

**29እኔ ችግረኛና ቍስለኛ ነኝ**
**አቤቱ፥ የፊትህ መድኃኒት ይቀበለኝ።**
**30የእግዚአብሔርን ስም በዝማሬ አመሰግናለሁ፥**
**በምስጋናም ከፍ ከፍ አደርገዋለሁ።**
**31ቀንድና ጥፍር ካበቀለ ከእምቦሳ ይልቅ**
**እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል።**
**32ችግረኞች ያያሉ ደስ ይላቸዋል**
**እግዚአብሔርን ፈልጉ ሕያዋንም ሁኑ።**
**33እግዚአብሔር ችግረኞችን ሰምቶአልና፥**
**እስረኞቹንም አልናቀምና።**

**69፡29-33** ይህ አንጓ የሚገልጸው የዳነው መዝሙረኛ የሚያደርገውን ነው፣ የያህዌ ማዳን ከፍ አድርጎ በደኅንነት ስላስቀመጠው።
1. የእግዚአብሔርን ስም በዝማሬ አመሰግናለሁ
2. በምስጋና ከፍ አደርገዋለሁ

ይህ የሚያመለክተው የመቅደስ መቼትን ነው፣ ቁጥር 31 ላይ እንዳለው (መሥዋዕት)። ቁጥር 9 ደግሞ የመቅደስ ጠቃሽ ነው (ማለትም፣ "ቤትህ" እና "እንደ መሥዋዕታዊ እሳት የተበላ")።
ያህዌ በሐሰት የተከሰሰውንና ያላግባብ የተደረገበትን መዝሙረኛ ማዳኑ፣ በሌሎቹ ላይ ደስታንና መታመንን በእርሱ ላይ ያደርጉ ዘንድ ምክንያት ሆነ (ዝኪ. ቁ. 32-33)።

**69፡29 "ችግረኛ"** ከዚህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 776) እና ካልተመደው ቃል፣ ቁ. 20 ላይ ካለው "ሕመምተኛ" ወይም "በተስፋ መቁረጥ ያለ፤" በርካታ አታቾች (ተርጓሚዎች) የሚያስረግጡት መዝሙረኛው መታመሙን ነው፣ ነገር ግን እኔ የማስበው ዐውደ-ጽሑፉ የሚገልጸው ስደትንና ሥነ-ልቦናዊ ጭንቀትን ነው፣ ሥጋዊ ሕመም ሳይሆን፣ ምንም እንኳ እነርሱ ዘወትር ቢያያዙም (ማለትም፣ ሳቢያና ውጤት)።
ደግሞም የሚቻለው የሕመም ዘይቤ የመዝሙረኛውን የኃጢአተኝነት ስሜት ማስረገጫ ሌለኛው መንገድ ሆኖ ነው ጥቅም ላይ የዋለው (ዝኪ. 69፡5)። ፈውስ ዘወትር የይቅርታ ፈሊጥ ነው (መዝ. 103፡3፤ ኢሳ. 1፡5-6)።

**69፡31** ይህ ቁጥር ከሥነ-መለኮት አኳያ በ70 ዓ. ም ድኅረ ይሁዲነት ጥቅም ላይ ውሏል "መሥዋዕት"ን በ "ምስጋና" ለመቀየር (መዝ. 40፡7፤ 50፡13-14፤ 51፡16-17)። ምስጋና እግዚአብሔርን ያስደስተዋል።

## መዝሙር ፡ 69፡34-36

**34ሰማይና ምድር ባሕርም**

> **በእርስዋም የሚንቀሳቀስ ሁሉ ያመሰግኑታል።**
> **35እግዚአብሔር ጽዮንን ያድናታልና፥ የይሁዳንም ከተሞች ይሠራልና**
> **በዚያም ይቀመጣሉ ይወርሱአትማል።**
> **36የባሪያዎቹ ዘር ይኖሩባታል።**
> **ስሙንም የሚወድዱ በዚያ ይቀመጣሉ።**

**69፡34-35** መዝሙር ላይ ተደጋግሞ እንደሚሆነው፣ በመጨረሻ አነስተኛ አንጓ አለ፣ ለአንድነት አምልኮ (ማለትም፣ መዝ. 103፡19-22)። የፍጥረት አምላክ የእስራኤልም አምላክ ነው፣ በጽዮን/ይሁዳ የሚኖር፣ ከሕዝቡ ጋር። የእነርሱም ባሕርይ

1. የባሪያዎቹ ዘር
2. ስሙን የሚወዱ

ይህ መዝሙር በዳዊት ጊዜ ቢሆን፣ እርሱ "እስራኤል" የሚል ይኖረው ነበር "ይሁዳ፣" ሳይሆን፣ አንዱም የለውም

1. ዳዊት አልጻፈውም (ማለትም፣ ከመዝሙራት ርዕሶች ጋር አይገጣጠምም፤ እነርሱ በሙት ባሕር ጥቅሎች ላይ አይገኙም፣ ደግሞም ዘወትር ከመዝሙር ጽሑፋዊ መረጃዎች ጋር አይገጥምም)
2. አንዱ ኋላ ላይ የመጨረሻውን አንጓ አክሎበታል፣ ከስደት በኋላ ሊሆን ይችላል።

**69፡34 "ሰማይና ምድር... ባሕርም"** እነዚህ ሦስት ስሞች ፍጥረትን ሁሉ ለመግለጽ ነው ጥቅም ላይ የዋሉት (ዘጸ. 20:4፣11፤ ዘዳ. 5:8፤ መዝ. 96:11፤ 135:6፤ 146:6፤ ሐጌ. 2:6)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በዚህ መዝሙር ላይ በአኪ የተጠቀሱትን ስፍራዎች ዘርዝር።
2. ለምን ተደጋግሞ ተጠቀሰ?
3. በዚህ መዝሙር ላይ የተዘረዘሩት ስሜቶች ከኢየሱስ አቋም የሚለዩት እንዴት ነው?
4. ወደ ኢሳይያስ 53 የሚያመለክቱ የሚመስሉትን ቁጥሮች ዘርዝር።
5. በዚህ መዝሙር ጥቅም ላይ የዋለውን የውኃ ተምሳሌት አብራራ።
6. የተጠቃለለው መደምደሚያ ኋለኛ ጭማሪ ነውን? እንደዛ ከሆነ፣ ተመስጧዊ ነውን?

# መዝሙር 70
# የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የዕርዳታ ጸሎት በአሳዳቾች ላይ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ። የዳዊት መዝሙር፤ ለመታሰቢያ | ጸሎት ከጠላቶች ለማረፍ | ጸሎት ከግል ጠላቶች ለመታደግ | የዕርዳታ ጸሎት | የጭንቀት ጩኸት |
| 70:1-3 | 70:1-3 | 70:1-3 | 70:1-3 | 70:1-2ለ |
| | | | | 70:2ሐ-3 |
| 70:4-5 | 70:4 | 70:4-5 | 70:4 | 70:4 |
| | 70:5 | | 70:5 | 70:5 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. "ፍጠን" የሚለው ቃል ተተኳሪ (ቢዲቢ 301፣ ኬቢ 300) መዝሙሩን መክፈቱን (ዝኪ. ቁ. 1b) እና መዝጋቱን (ዝኪ. ቁ. 5ለ) ተገንዘብ (ማለትም፣ አካታች (*inclusio*))። ግሡ መዝሙር 22:19፤ 38:22፤ 40:13፣17፤ 71:12 ላይ ተደግሟል።

ለ. ብዙ ያልተጠናቀቁዎች በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ተገንዘብ (ትይዩውን ተገንዘብ)።
1. አሉታዊ
   ሀ. ይፈሩ፣ ቁ. 2ሀ – ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*፣ መዝ. 35:4፤ 83:17
   ለ. ይጎስቁሉ፣ ቁ. 2ሀ – ቢዲቢ 344፣ ኬቢ 340፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*፣ መዝ. 40:14
   ሐ. ወደ ኋላቸው ይመለሱ፣ ቁ. 2ሐ – ቢዲቢ 690፣ ኬቢ 744፣ *ኒፋል ያልተጠናቀቀ*
   መ. ይፈሩም፣ ቁ. 2ሐ – ቢዲቢ 483፣ ኬቢ 480፣ *ኒፋል ያልተጠናቀቀ*
   ሠ. ወደ ኋላቸው ይመለሱ፣ ቁ. 3ሀ – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
2. አዎንታዊ
   ሀ. የሚሹህ ሁሉ በአንተ ሐሤት ያድርጉ፣ ቁ. 4 – ቢዲቢ 965፣ ኬቢ 1314፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
   ለ. የሚሹህ ይደሰቱ፣ ቁ. 4 – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
   ሐ. ማዳንህን የሚወዱ ይበሉ. . .፣" ቁ. 4ለ – ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
   መ. እግዚአብሔር ታላቅ ይሁን፣ ቁ. 4ሐ – ቢዲቢ 152፣ ኬቢ 178፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
   ሠ. አትዘግይ፣ ቁ. 5መ – ቢዲቢ 28፣ ኬቢ 34፣ *ፔል ያልተጠናቀቀ*

ሐ. የመዝሙሩን አስደናቂ ተመሳሳይ ትይዩ ተገንዘብ።

መ. ይህ መዝሙር በመጠነኛ ልዩነቶች ተደግሟል፣ መዝሙር 40:13-17 ላይ፣ ከቁጥር 3ሀ በቀር።
1. መዝሙር 70:3፣ "ይመለሱ" (ቢዲቢ 690 I)
2. መዝሙር 40:15፣ "በፍርሃት መንቀጥቀጥ" (ቢዲቢ 1030)

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 70፡1-3**

**[1]አቤቱ፥ እኔን ለማዳን ተመልከት**
**አቤቱ፥ እኔን ለመርዳት ፍጠን።**
**[2]ነፍሴን የሚሹአት**
**ይፈሩ ይጐስቍሉም፥**
**ከፉንም የሚመክሩብኝ**
**ወደ ኋላቸው ይመለሱ ይፈሩም።**
**[3]እንኳ እንኳ የሚሉኝ**
**አፍረው ወዲያው ወደ ኋላቸው ይመለሱ።**

**70፡1** አአመመቅ የሚለው ቃል ተተኳሪ ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ መዋሉን ነው (መዝ. 22፡19፤ 38፡22፤ 40፡13፤ 71፡12፤ 141፡1) እናም ትይዩ ነገሮች አሉት (ዝከ. ቁ. 5)።

1. አድነኝ
2. ዕርዳኝ

ደግሞም ተገንዘብ፣ እግዚአብሔር (ኤሎሂም) ከጌታ (ያህዌ) ጋር ትይዩ መሆኑን፣ ቁጥር 5 ላይ እንደሆኑት። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 1፡1 ላይ።

**70፡2 "መፍቀድ..."** ይህ የእንግሊዝኛ መንገድ ነው፣ ጥያቄን በተጽዕኗዊነት ለመግለጽ። ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ለን ተመልከት።

▣ **"መፈለግ"** ይህ ግሣዊ (ቢ.ዲ.ቢ. 134፣ ኬቢ. 152፣ ፔል አንቀጽ) ቁጥር 2 እና 4 ላይ ይከሰታል። እሱም ሁለት ዓይነት ሰዎችን ይገልጻል።

1. ሌሎችን ለመግደል የሚሹ፣ የራሳቸውን መንገድ ለማግኘት
2. እግዚአብሔርን የሚሹ

**70፡2-3 "እነርሱ..."** መዝሙረኛውን የሚቃወሙት ባሕርያቸው በሦስት ትይዩ ሐረጎች ላይ ተገልጿል።

1. ነፍሴን የሚሹ (ኔፊሽ)
2. በጉዳቴ ደስ የሚሰኙ
3. "እንኳ፣ እንኳ" የሚሉ

የመጨረሻው የተለመደውን የብኪ የአጻጻፍ ብልሃት ያሳያል፣ "የተገላቢጦሽ" የሚባለውን። በመልካሙ መዝሙረኛ ላይ እንዲሆን የተመኙት በእነርሱ ላይ ሆነ!

**መዝሙር ፡ 70፡4-5**

**[4]የሚሹህ ሁሉ በአንተ ሐሤት ያድርጉ ደስ ይበላቸው**
**ማዳንህን የሚወድዱ ሁልጊዜ።**
**እግዚአብሔር ታላቅ ነው ይበሉ።**
**[5]እኔ ችግረኛና ምስኪን ነኝ**
**አቤቱ፥ እርዳኝ**
**ረዳቴ ታዳጊዬም አንተ ነህ**
**አቤቱ፥ አትዘግይ።**

**70፡4 "የሚሹህ"** ይህ የብኪ ፈሊጥ ነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ለሚሆን ግላዊ የእምነት ግንኙነት፣ ባሕርዩም

1. የመቅደስ አምልኮ
2. የኪዳን ታዛዥነት

የቁጥር 4 የመጨረሻው ስንኝ የመቅደስ የአምልኮ ሥርዓት ሊሆን ይችላል።

**70፡5** ቁጥር 1 ላይ ያሉት ሁለቱ "አድን" እና "እርዳ" የሚሉት ጽንሰ-ሐሳቦች እንደተደገሙ ተገንዘብ (የተለየ ግን ተመሳሳይ ግሥ ለ"መታደግ")።

▣ **"እኔ ችግረኛና ምስኪን ነኝ"** መዝሙረኛው የገዛ ራሱን ታሳቢ ሁኔታ ነው የሚገልጸው። እግዚአብሔር ታላቅ ነው (ቁ. 4) እሱ ግን ተጎድቷል። እሱ እግዚአብሔርን ይጠይቃል፣ ለዕርዳታ ፈጥኖ እንዲመጣ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት _መመሪያ_ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙር 70 ለምን መዝሙር 40፥13-17 ላይ ሊገኝ ቻለ?
2. “የተገላቢጦሽን” ጽሑፋዊ ጽንሰ-ሐሳብ በገዛ ራስህ ቃላት አብራራ።
3. የመለኮት ስሞች የሆኑት *ኤሎሂም* እና *ያህዌ* አንድምታቸው ምንድነው?

# መዝሙር 71
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የሽማግሌ ጸሎት ለመታደግ<br><u>ኤምቲ መግቢያ የለውም</u> | እግዚአብሔር የደኅንነት ዐለት | የአማኝ ሽማግሌ ጸሎት ከግል ጠላቶች ለመታደግ | የሽማግሌ ሰው ጸሎት | የሽማግሌ ጸሎት |
| 71፡1-6 | 71፡1-3 | 71፡1-3 | 71፡1-3 | 71፡1-2 |
| | | | | 71፡3-4 |
| | 71፡4-6 | 71፡4-6 | 71፡4-6 | |
| | | | | 71፡5-6 |
| 71፡7-11 | 71፡7-8 | 71፡7-11 | 71፡7-11 | 71፡7-8 |
| | 71፡9-11 | | | 71፡9-10 |
| | | | | 71፡11-12 |
| 71፡12-16 | 71፡12-13 | 71፡12-16 | 71፡12-16 | |
| | | | | 71፡13 |
| | 71፡14-16 | | | 71፡14-15 |
| | | | | 71፡16-17 |
| 71፡17-21 -21 | 71፡17-18 | 71፡17-18ሠ | 71፡17-21 | |
| | | | | 71፡18መ |
| | | 71፡18ረ | | 71፡18ሠ-21 |
| | 71፡19-21 | | | |
| 71፡22-24 | 71፡22-24 | 71፡22-24 | 71፡22-24 | 71፡22-24 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 71፡1-6**
**1 አቤቱ፥ አንተን ታመንሁ**
**ለዘላለም አልፈር።**
**2 በጽድቅህ አስጥለኝ ታደገኝም**
**ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል አድነኝም።**

> [3]በጠንካራ ቦታ ታድነኝ ዘንድ
> አምላክና መሸሸጊያ ሁነኝ
> ኃይሌ መጠጊያዬ አንተ ነህና።
> [4]አምላኬ፥ ከኃጢአተኛ እጅ፥
> ከዓመፀኛና ከግፈኛም እጅ አድነኝ።
> [5]አቤቱ፥ አንተ ተስፋዬ ነህና፥
> እግዚአብሔር ሆይ፥ ከታናሽነቴ ጀምረህ መታመኛዬ ነህና።
> [6]ከማኅፀን ጀምሮ በአንተ ተደገፍሁ፥
> ከእናቴም ሆድ ጀምሮ አንተ መሸሸጊያዬ ነህ
> ሁልጊዜም ዝማሬዬ ለአንተ ነው።

**71፡1-6** ይህ የመግቢያ አንጓ የደራሲውን አመለካከት በግልጽ የሚያሳይ ነው። ኤምቲ መግቢያ አለመኖሩን ተገንዘብ። አብዛኞቹ አታቾች (ኮሜንታተርስ) የሚገምቱት ይህ የሽማግሌ ሰው ጸሎት እንደሆነ ነው (ዝከ. ቁ. 9፣18) እሱም የተሳደደ (ዝከ. ቁ. 4፣10፣13፣24)።

**71፡1 "መጠጊያ አደርጋለሁ"** ለዚህ ግሥ (ቢዲቢ 340፣ ኬቢ 337፣ *ቃል የተጠናቀቀ*)፣ መዝሙር 5፡11 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ መጠጊያ

"መጠጊያ" (ቢዲቢ 340፣ ኬቢ 337) ጥቅም ላይ የሚውለው ከማዕበል መጠለያ ለመውሰድ ሲሆን ነገር ግን ዘወትር በዘይቤነት ጥቅም ላይ የሚውለው፣ ከክፉ ሰዎች ለመጠበቅ ነው።

1. ግሥ ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ ውሏል፣ መዝ. 2፡12፤ 5፡11፤ 7፡1፤ 11፡1፤ 16፡1፤ 18፡2፤ 25፡20፤ 31፡1፣19፤ 34፡8፣22፤ 37፡40፤ 57፡1፤ 61፡4፤ 64፡10፤ 71፡1፤ 118፡8፣9፤ 141፡8፤ 144፡2 ላይ
2. ስሙ ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ ውሏል፣ መዝ. 14፡6፤ 46፡1፤ 61፡3፤ 62፡7፣8፤ 71፡7፤ 73፡28፤ 91፡2፣9፤ 94፡22፤ 142፡5 ላይ

የመጠጊያ ምስያ፣ ከነ ልዩነቱ ሁሉ፣ መዝሙር 18፡1-2 ላይ ይታያል!

▣ **"ፈጽሞ አልፈር"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116) *ቃል ተጓዳኝ* ነው። ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

## ልዩ ርዕስ፡ ኀፍረት (ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116) በሥነ-መለኮታዊ መልኩ

"ኀፍረት" የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ፍርድ ነው፣ በኃጢአት ላይ (ማለትም፣ ዘፍ. 2፡25 ከዘፍ. 3፡10 ጋር ሲነጻጸር)። መዝሙር 31፡17ሀ ከ31፡17ለ ጋር ያለውን ንጽጽር ተገንዘብ። ኀፍረት ከፍርድ ጋር ይያያዛል፣ መዝሙር 53፡5፤ 119፡1-8፣80፤ ዳን. 12፡2 ላይ።

ኀፍረት እንዲያው የአንዱ ዝና ወይም ኩራት ጉዳት አይደለም፣ ነገር ግን ጽኑ የሆነ የኪዳን መስፈርቶችን መጣስ ነው፣ እናም ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ኅብረት ማጣት። እሱም ዘወትር ለአመንዝሮች ነው ጥቅም ላይ የሚውለው (መዝ. 97፡7፤ ኢሳ. 42፡17፤ 44፡9፣11፤ 45፡16፤ ኤር. 51፡17)።

ለኀፍረት አለመኖር ታላቁ ተስፋ፣ በያህዌ ላይ እምነታቸውን ላሳረፉ ነው (ኢሳ. 49፡23፤ መዝ. 25፡3፤ ኢዩኤል 2፡27) በጳውሎስ ተደግሟል ሮሜ. 9፡33 እና በዮሐንስ፣ 1 ዮሐንስ 2፡28 ላይ።

**71፡2** ሁለቱ ቀዳሚዎቹ ግሦች "ማዳን" (ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ መዝ. 70፡1) እና "መታደግ" (ቢዲቢ 812፣ ኬቢ 93) ሁለቱም ያልተጠናቀቁ ናቸው፣ በሂደት ላይ ያለ ድርጊትን የሚገልጹ። ሦስተኛው ተመሳሳይ "ማዳን" (ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*) ቁጥር 2ለ ላይ አለ።

የጸሎቱን መሠረት ተገንዘብ (ማለትም፣ ሁለት ሂፊል ተተኳሪዎች፣ ቁ. 2ለ) የመዝሙረኛው የሥራ ውጤት አለመሆኑን ነገር ግን የያህዌ ጽድቅ እንጂ (ዝከ. ቁ. 16፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡5 ላይ)።

▣ **"ጆሮህን አዘንብል"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ *ሂፊል ተተኳሪ*) ሰዋዊ ዘይቤ መግለጫ መንገድ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 2፡4-6 ላይ) እግዚአብሔርን ለመለመን የመዝሙረኛውን ጸሎት እንዲሰማ (መዝ. 17፡6፤ 31፡2፤ 86፡1፤ 88፡2፤ 102፡2)። የዚህ መዝሙር ቀዳሚዎቹ ሦስት ቁጥሮች ከመዝሙር 31፡1-3 ጋር ተመሳሳይ ናቸው።

**71፡3 "የመጠጊያ ዓለት ሁነኝ"** የእግዚአብሔር ጽንሰ-ሐሳብ እንደ "ከፍታማ ጠጣር ዓለት" (ቢዲቢ 700፣ ማለትም፣ ምሽግ፣ ዝከ. ቁ. 3ሐ) መዝ. 18፡2፤ 31፡2-3፤ 40፡2 ላይ ይታያል፣ እሱም ከዘዳ. 32፡31፣37 ጋር ሊጣቀስ የሚችል።

"መጠጊያ" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ (ቢዲቢ 732) የሚገልጸው ከእግዚአብሔር ጋር መኖርያ ስፍራን ነው (ማለትም፣ ቤተ-መቅደስ፣ መዝ. 76፡2)፣ ከመዝ. 23፡6፤ 27፡4-6፤ 90፡1፤ 91፡9 ተመሳሳይ የሆነ። የመታደጉ ጸሎት የችግሮችና ጠላቶች አለመኖር ከሚለው እጅግ የሚልቅ ነው፣ የእግዚአብሔር መገኘት ስላለበት (ዘዳ. 33፡27)።

ሊሆን የሚችለው "የመጠጊያ/የመኖርያ ዓለት፣" מָעוֹן "የመሸሸጊያ ዓለት፣" ሊሆን ይችላል מָעוֹז (ቢዲቢ 731፣ መዝ. 31፡2)። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 305) ለ "መኖርያ" "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል (ሁነኛ ጥርጣሬ)።

▣ **"ታድነኝ ዘንድ ትእዛዝን ሰጠህ"** ግሥ (ቢዲቢ 845፣ ኬቢ 1010፣ *ፒል የተጠናቀቀ*) የሚተረጎመው እንደ

1. ያለፈ ትእዛዝ – አአመመቅ፣ አኪጀት፣ አኢመቅ፣ የተእመቅ

2. የወደፊት ወይም የአሁን ጥያቄ – ጀፒኤስአኤ

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ለ “ይመጣ ዘንድ ትእዛዝ ስጠህ” ለሚለው “ሐ” ደረጃ ነው የሚሰጠው (ማለትም፣ ሁነኛ ጥርጣሬ)። አእት መጽሐፍ ቅዱስ የሚደግፈው የዩቢኤስን ሌለኛ ምርጫ ነው፣ “ለተመሸገ መኖርያ” (የተመት፣ አየተመት)፣ መዝሙር 31፡2ን ተከትሎ።

**71፡4 “አድነኝ”** በእነዚህ ቀዳሚዎቹ አራት ቁጥሮች በርካታ ተመሳሳዮች ጥቅም ላይ ውለዋል።

1. አድን – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*፣ መዝ. 7፡1፤ 39፡9፤ 51፡14፤ 71፡11
2. ታደግ – ቢዲቢ 812፣ ኬቢ 930፣ *ፒል ያልተጠናቀቀ*፣ ቁ. 2፤ *ፒል ተተኳሪ*፣ ቁ. 4፣ መዝ. 18፡48፤ 22፡4፣8፤ 31፡1፤ 37፡40፤ 43፡1፤ 82፡4፤ 91፡14
3. አድን – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ ቁ. 2፤ *ሂፊል ያልተወሰነ አወቃቀር*፣ ቁ. 3፤ 57 ጊዜ መዝሙር ላይ ጥቅም ላይ ውሏል።

▣ **“እጅ”** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 7፡3-4 ላይ

▣ **“ኃጢአተኞች”** መዝ. 1፡5፤ 5፡10፤ 15፡2-5. እዚህጋ ጥቅም ላይ የዋሉትን ሦስት ቃላት ተገንዘብ።

1. ኃጢአተኛ – ቢዲቢ 957
2. ዓመጸኛ – ቢዲቢ 732
3. ግፈኛ – ቢዲቢ 330 III፣ ኬቢ 329

**71፡5-6** ገላጭ የሆኑትን ቃላት ተገንዘብ፣ “አዶናይ ያህዌ”ን ባሕርይ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን (“ጌታ ጌታዬ፣” ዝከ. ቁ. 16)።

1. ተስፋዬ – ቢዲቢ 876፣ መዝ. 39፡7፤ 62፡5፤ ኤር. 14፡8፤ 17፡13
2. መተማመኛዬ – ቢዲቢ 105 (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 4፡5 ላይ)
3. ደጋፊዬ (ተደግፌአለሁ) – ቢዲቢ 701፣ ኬቢ 759፣ *ኒፋል የተጠናቀቀ*፣ ኢሳ. 48፡2

▣ **“ከትንሽነቴ ጀምሮ… ከሕፃንነቴ ጀምሮ… ከእናቴ ሆድ ጀምሮ”** እነዚህ ትይዩ ሐረጎች ፈሊጣዊ መንገዶች ናቸው፣ የመዝሙረኛውን መተማመን የሚያስረግጡ፣ እግዚአብሔር ዘወትር ከእርሱ ጋር እና ለእርሱ እንደሆነ፣ (መዝ. 22፡9-10)! እነዚህ ለእስራኤል ጥቅም ላይ ውለዋል፣ ኢሳ. 46፡3።

**71፡6**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አየተመቅ** | ***“ወሰድከኝ”*** |
| **አኪጀት** | ***“አወጣኸኝ”*** |
| **ጀፒኤስአኤ** | ***“ደገፍከኝ”*** |
| **LXX** | ***“መጠጊያ”*** |

ኤምቲ “መቁረጥ” የሚል አለው (ቢዲቢ 159፣ ኬቢ 186፣ *ቃል አንቀጽ*)፣ እሱም ዘይቤአዊ ሊሆን ይችላል፣ እግዚአብሔር እትብትን ለመቁረጡ (ማለትም፣ ካልተወለደ ሕፃን ጋር የቀረበ ግንኙነት አለው፣ እንደ መዝ. 22፡9-10፤ 139፡13-16፤ ኤር. 1፡5)።

“ከ፣” “መሳብ፣” ወይም “ብርታት/ድጋፍ” (LXX) ሌለኛው አማራጭ ማረሚያን ያካትታል።

***መዝሙር ፡ 71፡7-11***

**[7]ለብዙዎች መደነቂያ ሆንሁ**
**አንተ ግን ብርቱ መጠጊያዬ ነህ።**
**[8]አፌን ምስጋና ምላ**
**ሁልጊዜ ክብርህንና ግርማህን እዘምር ዘንድ።**
**[9]በእርጅናዬ ዘመን አትጣለኝ፥**
**ጒልበቴም ባለቀ ጊዜ አትተወኝ።**
**[10]ጠላቶቼ በላዬ ተናግረዋልና**
**ነፍሴንም የሚሹአት በአንድነት ተማክረዋልና፥ እንዲህም አሉ።**
**[11]እግዚአብሔር ትቶታል**
**የሚያድነው የለምና ተከትላችሁ ያዙት።**

**71፡7-11** ይህ አንጓ የጻድቅ ሽማግሌን ፍርሃት ይገልጻል። በግልጽ እንደሚታየው የሽምግልና ሁኔታው ለአንዳንዶች እግዚአብሔር ለእርሱ የሚያደርገውን ክብካቤና መገኘቱን እንዲጠይቁ አድርጓቸዋል። መዝሙር ላይ “መታደግ” የሚለው ቃል (ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717) በዋነኛነት ለእግዚአብሔር ማዳን ጥቅም ላይ ውሏል።

**71፡7**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | ***“መገረም”*** |
| **አኪጀት** | ***“መደነቅ”*** |
| **አየተመቅ፣ የተእመቅ፣** | |
| **LXX** | ***“አስገራሚ”*** |
| **አእቅ፣ ጀፒኤስአኤ** | ***“ምሳሌ”*** |
| **አኢመቅ** | ***“መምታታት”*** |

የዕብራይስጡ ቃል (ቢዲቢ 68) ፍችው “አስደናቂ፣” “ምልክት፣” ወይም “ማሳያ” ነው። ቢዲቢ የእሱን አጠቃቀም እዚህጋ የሚመለከተው እንደ የተለየ፣ “በያህዌ እንደሚጠበቅ ሰው” በማመላከት ነው፣ እሱም ቁጥር 6ን የሚጠቅስ።

**71፡8** ይህ ቁጥር የቁጥር 6ን የመዝጊያ ስንኝ ትይዩ ያደርጋል። የዚህ ሰው ሕይወት “የምስጋና” ባሕርይ ነበረው (ቢዲቢ 239፣ ዝከ. ቁ. 14፤ Ps. 34:1)።

**71፡9** ምንም እንኳ ይህ ሰው የእምነትና የምስጋና ሰው ቢሆንም፣ ሽምግልናና የጠላቶቹ ቃላት እንዲፈራና እንዲጨነቅ አድርጎታል (ዝከ. ቁ. 18)። ይህ ፍርሃት የሚገለጸው በሁለት ያልተጠናቀቀ ነው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ።

1. አትጣለኝ – ቢዲቢ 1020፣ ኬቢ 1527፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ*፣ መዝ. 51:11
2. አትተወኝ – ቢዲቢ 736፣ ኬቢ 806፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*

**71፡10-11** እነዚህ ቁጥሮች የሚገልጹት የመዝሙረኛው ጠላቶች የሚሉትን ነው (ወይም ቢያንስ እሱ የሚለው የእነርሱ ሐሳብ)።

1. እግዚአብሔር ትቶታል – ቢዲቢ 736፣ ኬቢ 806፣ *ቃል* የተጠናቀቀ (ቋሚ የመተው ሁኔታ)
2. ተከተሉት – ቢዲቢ 922፣ ኬቢ 1191፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. ያዙት – ቢዲቢ 1074፣ ኬቢ 1779፣ *ቃል ተተኳሪ*
4. የሚያድነው የለምና – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል* አንቀጽ

መዝሙር 3፡2 ደግሞ የሚገልጸው የእግዚአብሔር ታማኝ ተከታይ ሆነው በጥርጥር ውስጥ ያሉትን የሚያጠቁት ሰዎች ክፉ አነጋገር ነው።

***መዝሙር ፡ 71፡12-16***

**12አምላክ ሆይ፥ ከእኔ አትራቅ**
**አምላኬ ሆይ፥ እኔን ለመርዳት ፍጠን።**
**13ነፍሴን የሚቃወሙአት ይፈሩ ይጥፉም፥**
**ጕዳቴንም የሚፈልጉ እፍረትንና ኀሣርን ይልበሱ።**
**14እኔ ግን ሁልጊዜ ተስፋ አደርጋለሁ፥**
**በምስጋናህም ሁሉ ላይ እጨምራለሁ።**
**15ሥራን አላውቅምና**
**አፌ ጽድቅህን**
**ሁልጊዜም ማዳንህን ይናገራል።**
**16በእግዚአብሔር ኃይል እገባለሁ**
**አቤቱ፥ ጽድቅህን ብቻ አስባለሁ።**

**71፡12-16** ይህ አንጓ ሦስት ገጽታዎች አሉት።

1. የመዝሙረኛው ጸሎት፣ ቁ. 12
   ሀ. ለእግዚአብሔር መገኘት (“ከእኔ አትራቅ”) – ቢዲቢ 934፣ ኬቢ 1221፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ መዝ. 22:11፣19
   ለ. ለእግዚአብሔር ፈጣን ዕርዳታ – ቢዲቢ 301፣ ኬቢ 300፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. የመዝሙረኛው ጸሎት ለጠላቶቹ ፍጻሜ ቁ. 13
   ሀ. ይፈሩ – ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   ለ. ይጥፉ – ቢዲቢ 477፣ ኬቢ 476፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   ሐ. እፍረትን ይልበሱ – ቢዲቢ 741፣ ኬቢ 813፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   መ. ኀሣርን ይልበሱ — ከሐ ጋር ተመሳሳይ ግሥ ይመስላል
3. የመዝሙረኛው ጽኑ እምነት፣ ቁ. 14-16
   ሀ. እኔ ግን ሁል ጊዜ ተስፋ አደርጋለሁ
   ለ. ምስጋናህንም... እጨምራለሁ
   ሐ. እናገራለሁ (ማለትም፣ በመቅደስ)
      (1) ጽድቅህን
      (2) ማዳንህን
      (3) ብርቱ ሥራህን
      (4) ጽድቅህን፣ ያንተን ብቻ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት (አንድ አምላክ) መዝ. 2፡7 ላይ)

**71፡15 “አፌ ይናገራል”** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765፣ ፒል ያልተጠናቀቀ) ዘወትር መዝሙር ላይ ጥቅም ላይ ይውላል፣ የያህዌን ባሕርይና ሥራውን ለማወጅ፣ በአምልኮ መቼት (ማለትም፣ መቅደስ)።

1. ድንቆቹን – መዝ. 9:1፤ 26:7፤ 40:5፤ 75:1፤ 78:4
2. ምስጋናውን – መዝ. 9:14፤ 79:13፤ 107:21
3. ድርጊቱን – መዝ. 66:16፤ 118:17፤ 145:6፣12
4. ጽድቁን –መዝ. 71:5 (ዝከ. 35:28፤ 40:10)
5. የኪዳን ፍቅሩንና ታማኝነቱን – መዝ. 88:11 (ዝከ. 40:10)
6. ክብሩን – መዝ. 19:1፤ 96:3 (ዝከ. 145:12)
7. ታላቅነቱን –መዝ. 145:6
8. መሲሑን – መዝ. 2:7
9. ስሙን – መዝ. 22:22፤ 102:21

እዚህ ይህ ቁጥር — ጽድቁን እና ማዳኑን ነው።

▣ **"የእነርሱን ድምር አላውቅምና"** ይህ ሐረግ ሊያንጸባርቅ የሚችለው

1. ተመሳሳይ እውነት እንደ መዝ. 40፡5፤ 139፡18፣ ማለትም የእግዚአብሔር አስደናቂ ሥራዎች እጅግ ብዙ ናቸው፣ ሊደረስባቸው የማይችል
2. ተመሳሳይ እውነት እንደ ኢዮብ 42:3፤ መዝ. 139:6፣ እነርሱ ከሰው መረዳት በላይ ናቸው
3. እሱም ማለት "ጻፍ" ነው፣ እንደ "ንገር" ተቃራኒ (ኒዶቴ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 1288)

**መዝሙር ፡ 71፡17-21**

17 **አምላኬ፥ ከታናሽነቴ ጀምረህ አስተማርኸኝ**
**እስከ ዛሬም ተአምራትህን እነግራለሁ።**
18 **እስካረጅም እስክሸመግልም ድረስ፥**
**ለሚመጣ ትውልድም ሁሉ**
**ክንድህን ኃይልህንም ጽድቅህንም እስክነግር ድረስ፥ አቤቱ፥ አትተወኝ።**
19 **አቤቱ፥ እስከ አርያም ታላላቅ ነገሮችን አደረግህ**
**አምላክ ሆይ፥ እንደ አንተ ያለ ማን ነው?**
20 **ብዙ ጭንቀትንና መከራን አሳይተኸኛልና፥**
**ተመለስህ ሕያውም አደረግኸኝ**
**ከምድር ጥልቅም እንደ ገና አወጣኸኝ።**
21 **ጽድቅህንም አብዛው፥ ተመልሰህም ደስ አሰኘኝ፥**
**ከጥልቅም እንደ ገና አወጣኸኝ።**

**71፡17-21** ይህ አንጓ የመዝሙሩን ማዕከላዊ ጭብጦች የሚቀጥል ነው። እሱም መዝሙረኛው ስለ እግዚአብሔር ባሕርይ እና ስለ ምሕረቱ ርግጠኝነት ያለውን እወጃ ይገልጻል። ከዚህ የተነሣ እሱ የእግዚአብሔርን ታላቅነት ይናገራል (ማለትም፣ በመቅደስ መቼት)።

**71፡17ሀ** እስራኤላውያን በሙሴ ታዘዋል፣ ለልጆቻቸው ስለ እግዚአብሔር እንዲያስተምሩ (ዘጸ. 10:12፤ 12:26፤ 13:8፣14፤ ዘዳ. 4:9፤ 6:7፣20-25፤ 11:19፤ 31:13፤ 32:46)። ስኬታማ እምነት ለቀጣዩ ትውልድ እምነት ቅድሚያ ይሰጣል!

**71፡17ለ "ተአምራትህን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9፡1 ላይ።

**71፡18** መስመር 1 የቁጥር 9 ድጋሚ ነው። መዝሙረኛው የእርሱ መልእክት፣ ስለ እግዚአብሔር ያለው፣ የእርሱንም ሆነ የሚመጣውን ትውልድ እንደሚረዳ ያስብ እንደነበር ተገንዘብ። በዚህ መልኩ ነው ቅዱስ ቃሉ እንዲሠራ የታቀደው!

**71፡19 "እስከ አርያም የሚደርስ"** ይህ የእግዚአብሔርን የፍጥረትና የመዋጀት ሥራ የሚገልጽ ፈሊጥ ነው፣ እጅግ ታላቅና ጠቀሚ የሆነና እስከ ደመናት የሚደርስ (መዝ. 57፡10)።

▣ **"እንደ አንተ ያለ ማን ነው?"** ይህ የያህዌን የተለየነት የሚጠቅስ ነው፣ በብዙ አምላክ አምላኪነት፣ በሄኖቴሲዝም፣ ሁሉም ነፍስ አለው በሚል ማኅበረሰብ መካከል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት መዝ. 2፡7 ላይ)። ይህም የእስራኤል የተለየነት አስተሳሰብ ነው!

**71፡20** ይህ መግለጫ ነው (በብኪ. ቃላት) የሰው ልጆች የተጋረጠባቸውን የሚያሳይ በዚህ በወደቀው ዓለም። "የሁለቱ መንገዶች" ሥነ-መለኮት (መዝሙር 1፤ ዘዳ. 30፡15፣19) ሕይወትን አያብራራም (መዝሙር 37፤ 73፤ እና ኢዮብ)።

▣ **"ተመለስህ... እንደ ገናም አወጣኸኝ"** እነዚህ የመመለስ ዘይቤዎች ይመስላሉ፣ ወደ ብርቱ ሕይወት፣ ትንሣኤ ሳይሆን። ብኪ ከሞት በኋላ ሕይወትን ያስረግጣል (ኢዮብ 14:14-15፤ 19:25-27፤ ዳን. 12:2)፣ ነገር ግን እዚህጋ ዐውደ-ጽሑፉ ለዚህ ጽንሰ-ሐሳብ ፍንጭ አይሰጥም።

▣ **"እኔ"** ሊሆን የሚችለው የብዙ ቁጥሩ "እኛ" በዚህ ጽሑፍ ላይ እንደሚሆን ነው። እንደዚያ ከሆነ ይህኛው ሌላው የወል ማጠቃለያ ምሳሌ ነው፣ ለግለሰብ መዝሙር። እንግዲያውስ እሱ ከሕዝቅኤል 37 ጋር ትይዩ ይሆናል (ማለትም፣ ብሔራዊ ተሐድሶ)።

**መዝሙር ፡ 71፡22-24**

22 **እኔም በበገና ስለ እውነትህ አመሰግንሃለሁ**
**የእስራኤል ቅዱስ አምላክ ሆይ፥**
**በመሰንቆ እዘምርልሃለሁ።**
23 **ዝማሬን ባቀርብሁልህ ጊዜ ከንፈሮቼ ደስ ይላቸዋል፥**
**አንተ ያዳንሃትም ነፍሴ።**
24 **ጉዳቴን የሚሹ ባፈሩና በተነወሩ ጊዜ**
**አንደበቴ ደግሞ ሁልጊዜ ጽድቅህን ይናገራል።**

**71፡22-24** መዝሙረኛው ሌዋዊ ዘማሪ የነበረ ሊሆን ይችላል (ዝከ. ቁ. 22)። እሱም እግዚአብሔርን ያመሰግናል ስለ ታማኝነቱ/እውነት (ቢዲቢ 54፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 12:1 ላይ)፣ ግን ደግሞ ስለ እፍረትና ውርደት፣ በጠላቶቹ ላይ ስለሚያመጣባቸው (ቁ. 24)።

▣ **"የእስራኤል ቅዱስ"** ይህ የኪዳን መጠሪያ ነው፣ ለያህዌ (መዝ. 78:41፤ 89:18፤ እጅግ በተደጋጋሚ በኢሳይያስ ላይ፣ ማለትም፣ 1:4፤ 5:24)። ልዩ ርዕስ ተመልከት: ቅዱስ መዝ. 16:3 ላይ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር በሽማግሌ ሰው እንደተጻፈ ሊታመን ቻለ?
2. ቁጥር 3 ከመዝሙር 23፡6 ጋር እንዴት ሊዛመድ ቻለ?
3. ቁጥር 5-6 ከኤርምያስ 1፡5 ጋር እንዴት ሊዛመድ ቻለ?
4. "መደነቅ" የሚለውን ቃል ቁጥር 7 ላይ፣ ግለጽ።
5. "ያፈሩ" ቁጥር 13 ላይ ግለጽ።
6. ቁጥር 19ሐ አህዳዊነትን ያስተምራልን?
7. ቁጥር 20 የሚጠቅሰው ፈውስን፣ የብርታት መመለስን ነው የሚጠቅሰው ወይስ ትንሣኤን?

# መዝሙር 72
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጻድቅ ንጉሥ አገዛዝ | የመሲሑ አገዛዝ ክብርና ሁለንተናዊነት | እግዚአብሔር ንጉሡን እንዲባርከው መጸለይ | ጸሎት ለንጉሥ | ተስፋ የተገባለት ንጉሥ |
| ኤምቲ መግቢያ የሰሎሞን መዝሙር | | | | |
| 72:1-4 | 72:1-4 | 72:1-4 | 72:1-5 | 72:1-2 |
| | | | | 71:3-4 |
| 72:5-7 | 72:5-7 | 72:5-7 | | 72:5-6 |
| | | | 72:6-7 | |
| | | | | 72:7-8 |
| 72:8-11 | 72:8-11 | 72:8-11 | 72:8-11 | |
| | | | | 72:9-10ለ |
| | | | | 72:10ሐ-11 |
| 72:12-15 | 72:12-15 | 72:12-14 | 72:12-14 | 72:12-13 |
| | | | | 72:14-15 |
| | | 72:15-17 | 72:15-17 | |
| 72:16-17 | 72:16 | | | 72:16 |
| | 72:17 | | | 72:17 |
| 72:18-19 | 72:18-19 | 72:18-19 | 72:18-19ለ | 72:18-19 |
| | | | 72:19ሐ | |
| 72:20 | 72:20 | 72:20 | 72:20 | 72:20 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ የተራዘመ ጸሎት ነው (ማለትም፣ "ስጥ" – ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ *ቃል ተተኳሪ*) ለጻድቁ ንጉሥና ለልጁ (2 ሳሙኤል 7 የሚጠቅስ ሊሆን ይችላል፣ በመዳረሻው መሲሑን የሚጠቅሰውን)።
1. ፍርዶችህ – አአመመቅ፣ አኪጀት፣ ጀፒኤስኦኤ
   – ፍትሕህ – አየተመቅ፣ የተእመቅ፣
   – የገዛ ራስህ ፍትሐዊ ፍርድ – አኢመቅ
2. ጽድቅህ – አአመመቅ፣ አኪጀት፣ አየተመቅ፣ ጄፒኤስኦኤ፣ የተእመቅ
   – የገዛ ራስህ የማዳን ፍትሕ፣ አኢመቅ

ለ. ይህ መዝሙር የብኪን "የአዲሱን ዘመን" መረዳት ያሳያል። የኪዳን መስፈርቶችና ተስፋዎች ፍሬ አፍርተዋል። የንግሥና ውዳሴ ከሆነ፣ ንጉሣዊ ግነት ነው፣ ነገር ግን የአዲሱ ዘመን ምናብ ከሆነ በክርስቶስ ፍጻሜ አግኝቷል። ይህ መዝሙር በብኪ አልተጠቀሰም፣ ነገር ግን አይሁድና የክርስቲያን ምንጮች እንደ መሲሐዊ ይወስዱታል። አልፍሬድ ኢደርሺምን ተመልከት፣ *የመሲሑ ኢየሱስ ሕይወትና ጊዜ*፣ *ዕዝል* IX፣ *ገጽ* 719 ተመልከት።

ሐ. ይህ መዝሙር ባልተጠናቀቁ ግሦች ተሞልቷል። አአመመቅ፣ አየተመቅ፣ እና ጄፒኤስኦኤ ቁጥር 2-4፣5-7፣8-11፣15-17፣19 ተመልከት፣ እንደ ያልተጠናቀቁ፣ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ (ማለትም፣ "እንደ..." "እንዲ...") ነገር አኪጀት እና አኢመቅ ሁሉንም የሚመለከቷቸው እንዳልተጠናቀቁ ነው (ማለትም፣ መሲሑ የሚያደርጋቸው ነገሮች)። አራት ተጽዕኗዊዎች በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ላይ አሉ (ማለትም፣ ቁ.፣ 8፣15፣16፣17)።

መ. ቁጥር 20 የማጠቃለያ ቃል ነው በኋለኛ አዘጋጅ/አጠናቃሪ፣ የመጽሐፍ ሁለት (ማለትም፣ መዝሙር 42-72) የመዝሙሩ። ደግሞም ሊሆን የሚችለው ቁጥር 18-19 የመዝጊያ ውዳሴ ይዟል፣ የመጽሐፍ ሁለት፣ የመዝሙሩ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 72፡1-4**

**[1]አቤቱ፥ ፍርድህን ለንጉሥ ስጥ፥**
**ጽድቅህንም ለንጉሥ ልጅ፥**
**[2]ሕዝብህን በጽድቅ፥**
**ችግረኞችህንም በፍርድ ይዳኝ ዘንድ።**
**[3]ተራሮችና ኰረብቶች**
**ለሕዝብህ ሰላምን ይቀበሉ።**
**[4]ለችግረኞች ሕዝብ በጽድቅ ትፈርዳለህ**
**የድሆችንም ልጆች ታድናለህ**
**ክፉውንም ታዋርደዋለህ።**

**72፡1-4** ይህ አንጓ ለአዲሱ ንጉሥ መልካም ሁኔታ ይጸልያል (ማለትም፣ መሲሕ) እንዲገዛ።

1. እንዲፈርድ (የብዙ ቁጥር ኤምቲ ላይ ሊሆን ይችላል፣ ጥራትን የሚገልጽ፣ ኢሳ. 9፡7፤ 11:2-5፤ 32፡1፤ ለ "ጽድቅ" ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡5 ላይ
2. በፍትሕ እንዲፈርድ (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 9፡5-6)፣ መዝ. 82፡3
3. ሰላምን እንዲያመጣ (የጻድቅ ንጉሥ አገዛዝ ምድሪቱ እንድትበለጽግ ያደርጋል፣ ማለትም፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)
4. ጽድቅ፣ ኢሳ. 11፡4
5. ማዳን
6. ክፉውን መስበር

የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን የተለያዩ ቃላት ተገንዘብ።

1. ሕዝብህ፣ ቁ. 2
2. ችግረኞችህም፣ ቁ. 2፣4 (ጄፒኤስኦኤ፣ "የተዋረዱት")
3. የችግረኞች ልጆች፣ ቁ. 4

ሁሉም የእግዚአብሔር ቤተሰቦች ይጠበቃሉ ይበረታታሉም።

በኪዳን ማኅበረሰብ ውስጥ በሀብታምና በደሀ መካከል ተቃርኖ እየጎለበተ መጥቷል። ይህ ተቃርኖ የተላለፈው ከስደቶቹ በኋላ ነው፣ በሚያምኑት፣ ታማኝ ተከታዮች እና ጣዖት አምላኪ ወራሪዎች/ገዥዎች። የተቸገሩት/ድሆች/ምስኪኖች ናቸው የሚታደሱት። ያህዌ ይንከባከባቸዋል ይከላከልላቸዋልም (የጎለበቱት የዘዳግም ጭብጦች)። እሱ የእነርሱ ብቸኛ ተስፋ እና አዳኝ ነው (መዝ. 103:6፤ 146:7)።

**72፡3** ይህ ምስያ በርካታ ፍችዎች ሊኖሩት ይችላሉ።

1. ተራራዎች... ኮረብቶች መልካም መሪዎችን ይጠቅሳሉ
2. ተራራዎች... ኮረብቶች እንደ ሰውኛ የብልጽግና መልእክተኞች ጥቅም ላይ ይውላሉ (ማለትም፣ የኪዳን በረከቶች)
3. ተራራዎች... ኮረብቶች የተስፋይቱ ምድር የጸና መረጋጋትን ይጠቅሳሉ

▣ **"ውኃ"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 284፣ ኬቢ 283) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪጋ። እሱም *ከሂፊል ግሥ* "ነጠብጣብ" የሆነ ይመስላል፤ በዓረብኛ የሥሩ ፍቺ "የሚፈስስ ዕንባ" ነው።

**መዝሙር ፡ 72፡5-7**

**[5]ፀሐይ በሚኖርበት ዘመን ሁሉ፥**
**በጨረቃም ፊት ለፊት ለልጅ ልጅ ይኖራል።**
**[6]እንደ ዝናብ በታጨደ መስክ ላይ፥**
**በምድርም ላይ እንደሚንጠባጠብ ጠብታ ይወርዳል።**

[7]**በዘመኑም ጽድቅ ያብባል፥**
**ጨረቃም እስኪያልፍ ድረስ ሰላም ብዙ ነው።**

**72፡5-7** ይህ አንጓ ለሁለት ጥያቄዎች አጽንዖት ይሰጣል።

1. የእግዚአብሔር ሕዝብ እሱን በመፍራት/በማክበር እንዲቀጥሉ
2. ይህም መሰጠት በጊዜ ውስጥ እንዲቀጥል (ማለትም፣ ፀሐይ እና ጨረቃ በሚኖሩበት ጊዜ ሁሉ፣ ዘፍ. 8፡22፤ መዝ. 89፡36-37)

እነርሱም ይህን ካደረጉ፣ እንግዲያውስ የበረከት ተስፋ ከሙሴ ኪዳን ይቀጥላል (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)። ንጉሡና ሕዝቡ (መዝ. 1፡9፤ 2፡12) ከኪዳኑ ሁኔታዎች ጋር መግጠም ይኖርበታል።

**72:5**

**አአመመቅ፣ ጀፒኤስኦኤ** **"እነሱን"**
**አኪጀት** **"እነሱ"**
**አየተመቅ፣ አኢ.መቅ፣**
**የተእቅ፣ LXX** **"እሱ"**

ኤምቲ የብዙ ቁጥር አለው፣ ስለዚህ፣ ሊያመለክት የሚችለው

1. የኪዳኑ ሕዝቦች አክብሮት
2. የመሲሐዊው ንጉሥ (ማለትም፣ የግርማው ብዙኅነት) አክብሮት

**▣**

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**
**የተእመቅ፣ ጀፒኤስኦኤ** **"ፍርሃት"**
**አየተመቅ፣ አእመቅ** **"መኖር"**
**አእቅ** **"አምልኮ"**
**አኢ.መቅ፣ LXX** **"መኖር"**

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 309) ለ "መጨረሻ" "ሐ" ደረጃ ይሰጣል (ሁነኛ ጥርጣሬ)። ይህም LXXን ይከተላል። እሱም ከትይዩው ጋር በተሻለ ይገጥማል።

***መዝሙር ፡ 72፡8-11***

[8]**ከባሕር እስከ ባሕር ድረስ፥**
**ከወንዝም እስከ ምድር ዳርቻ ድረስ ይገዛል።**
[9]**በፊቱም ኢትዮጵያ ይሰግዳሉ፥**
**ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ።**
[10]**የተርሴስና የደሴቶች ነገሥታት ስጦታን ያመጣሉ**
**የዓረብና የሳባ ነገሥታት እጅ መንሻን ያቀርባሉ።**
[11]**ነገሥታት ሁሉ ይሰግዱለታል።**
**አሕዛብም ሁሉ ይገዙለታል።**

**72፡8-11** የመሲሑ አገዛዝ የሚሆነው

1. ሁለንተናዊ (ማለትም፣ የጥቅምን (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ቃላትን በመጠቀም)
   ሀ. ከባሕር ወደ ባሕር (ዘካ. 9፡10)
   ለ. ከወንዝ (ማለትም፣ ኤፍራጥስ) እስከ ምድር ዳርቻ (ማለትም፣ ሰሎሞን ይህንን አካባቢ ገዝቶታል)
2. ሰዎች ሁሉ ያከብሩታል፣ እጅ-መንሻም ያመጣሉ፣ ኢሳ. 49፡23

ይህ ሁለንተናዊ አገዛዝ (መዝ. 2:8፤ 59:13፤ 65:2፤ 67:7፤ ኢሳ. 45:22፤ 52:10፤ ሚኪያስ 5:4) ከዘፍ. 1:26-27 እና 12:3 ማጠቃለያ እንደሆነ ግልጽ ነው። አሀዳዊነት እውነት ከሆነ፣ የአዳም ልጆች ሁሉ መዋጀት ግብ ይሆናል (ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ፤ መዝሙር 2 ሌለኛው መሲሐዊ መዝሙር ነው)።

**72:9**

**አአመመቅ** **"ዘላኖች"**
**አኪጀት (MT)** **"በምድረ-በዳ የሚኖሩ"**
**አየተመቅ** **"ጠላቶች"**
**አእቅ** **"የምድረ-በዳ ሰዎች"**
**አኢ.መቅ** **"አውሬዎች"**
**LXX** **"ኢትዮጵያውያን"**
**የተእመቅ** **"የምድረ-በዳ ነገዶች"**

ቃሉ ( צִי ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 850 II፣ ኬቢ. 1020) የሚኖረው ፍች

1. ጠላቶች ከ צִיִּים ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 865 III (የታረመ፣ ነገር ግን ከትይዩው "ጠላቶች" ጋር የሚገጥም ከቁ. 9ለ ጋር በተሻለ)
2. የምድረ-በዳ አውሬዎች – መዝ. 74:14፤ኢሳ. 13:21፤ 23:13፤ 34:14፤ ኤር. 50:39 (ከ צִיָּה ፣ "ደረቅነት፣" ኤር. 50:12፤ 51:43)

3. ሊሆን የሚችለው (አእመቅ) ቁ. 2 የሚጠቅሰው የምድረ-በዳ አጋንንትን ነው (ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት)
4. ልዑካን ወይም መልእክተኛ – ገ'ჴ (ቢ.ዲ.ቢ. 851 II)፣ ኢሳ. 18:2

## ልዩ ርዕስ፡ አጋንታዊ (ርኩስ መንፈስ)

ሀ. በወደቁት መላእክትና በአጋንንት መካከል ያለው ግንኙነት ምን እንደሆነ አይታወቅም፡፡ 1ሔኖክ በዘፍጥረት 6፡1-8 ያለው *ነፊሊም* የክፋት ምንጭ መሆኑን ያረጋግጣል፡፡ ረቢዎችም በዘፍጥረት 3 ያለው ፅሁፍን ሳይሆን በዚህ ላይ ያተኩራሉ፡፡ 1 ሔኖክ እነዚህ ግማሽ ሰውና ግማሽ መንፈስ የሆኑ ፍጥረታት በጥፋት ውሃ እንደሞቱ ይናገራል፡፡ በጠጨማሪም የጥፋት ውሃው የመጣው ከእነዚህ ምክንያት የተነሳ መሆኑን ይናገራል፡፡ግን አካል የሌላቸው መናፍስት የሚሸከማቸውን አካል እየፈለጉ ናቸው፡፡

ለ. ብሉይ ኪዳን ውስጥ የተለያዩ ስም ያላቸው አጋንንትና ጠላት የሆኑ መናፍስት አሉ፡፡

1. *Satyrs* ሳቴየርስ (ጣኦታት ወይም ጸጉራማ አጋንንት (BDB 972 III) ፣ ዘሌ.17÷7፤ 2ኛ ዜና 11÷15)
2. *Shedim* ሽዲም (BDB 993) – ዘዳ. 32:17፤ መዝ. 106:37፣ መስዋዕት የሚሰዋለቸው (ከ*ሞሎክ Molech* ጋር ተመሳሳይ ነው)
3. *Lilith* ሊሊስ (BDB 539) (ሴት የማታ አጋንንት፣ ኢሳ.34÷14 ከኡጋርትና ከባቢሎናውያን አፈታሪክ ክፍል የሆነ)
4. *Az'azel* አዛዜል የበረሃ ጋኔን( 1 ሔኖክ 8:1 9:6፤ 10:4-8፤ 13:1-2፤ 54:5፤ 55:4፤ 69:2 ውስጥ በጣም የታወቀ አለቃ) – ሌዋ. 16:8 ፣10፣ 26
5. መዝ 91:5-6 የሚያስጠሉ ክፉ ነገሮች ተገልጠዋለወ (ቁጥር 10) መንፈሳዊ አካላት አይደሉም፡፡(መኃልዬ 3:8)
6. ኢሳያስ 13:21 እና 34:14 ላይ የተለያዩ የበረሃ እንስሳት ተዘርዝረዋል፡፡ በዚህ መንገድ የተተወ የተደመሰሰ ና የጠፋ ቦታ ለማሳየት፡፡ በዚህ ዝርዝር አጋንንትን እንደየሚያሳይ የሚያስቡ ሰዎች ይህ ቦታ በአጋንንት የሚጎበኝ ቦታ እንደሆነ ይገምታሉ፣ ማቴ. 12:43፤ ሉቃ 11:24 ራዕይ. 18:2)

ሐ. የብሉይ ኪዳን አንድ አምላክ (monotheism) አመለካከት የአረማዊያንን አፈታሪክ አበዝምታ አልፎታል ግን አንዳንዴ የነሱን ጥንቆላ ስም የሰጣቸዋል (የቅኔ ፅሁፎች) የክፉ መናፍስት እውነታ ቀስ በቀስ እየተገለጠ የመጣ ሲሆን በአዲስ ኪዳን ውስጥ በመልአክ/ሰይጣን ሆኖ ተገልጧል፡፡

◘ **"ጠላቶቹም አፈር ይልሳሉ።"** ይህ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ስዕል ነው (ማለትም፣ የግድግዳ ቅርጽ እና ስዕሎች) አንዱ ወደ ምድር አጎንብሶ (ዝከ. ቁ. 9ሀ)። ለዚህም "አፈር መላስ" የሚል ጽሑፋዊ ፈሊጥ ታክሎበታል (ቢ.ዲ.ቢ. 535፣ ኬቢ. 525፣ ፒል ያልተጠናቀቀ፣ ኢሳ. 49:23፤ ሚኪያስ 7:17)፣ ይኸውም የአንዱን መሸነፍ እና መረታት በመጎንበሱ የሚያመላክት።

**72፡10 "ተርሴስ"** የቦታ ስም (ቢ.ዲ.ቢ. 1077) ሊያመለክት የሚችለው
1. በደቡብ ስፔን ወደ አትላንቲክ ሲል የሚገኝ ከተማ፣ እሱም የፍቂያውያን ቅኝ-ግዛት የነበረ (ማለትም፣ ታርቲሰስ፣ ቁጥር 7)
2. የሳርዲኒያ ደሴት (ዘፍ. 10፡4)
3. በሰሜን አፍሪካ ባሕር ዳርቻ የሚገኝ ከተማ (ካርቴጅ የፍንቄ ቅኝ-ግዛት ነበር)
4. ራቅ ያለ ወደብ የሚጠራበት ዘይቤ
5. ተለቅ ያለ የንግድ መርከብ ዓይነት
6. ባላንጣ የመርከብ ንግድ የሚያካሂድ አገር (1 ነገ. 10፡22)

◘ **"ደሴቶች"** ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 15 I) የዘወትር ፍችው "የባህር ዳርቻ" ወይም "ደሴት" ነው። እሱም ራቅ ያሉ አገሮችን ያመለክታል (ኢሳ. 40:15፤ 66:19፤ ኤር. 25:22፤ 31:10)። ይህም ከዚህ አንጓ ምስያ ጋር ይገጥማል (ማለትም፣ የመሲሑ ሁለንተናዊ አገዛዝ)።

◘ **"ሳባ"** ይህ ከካም የሆነ ሕዝብን ወይም ነገድን ያመለክታል፣ በደቡብ ዓረብ የሚኖር።

◘ **"ሴባ"** ይህ የሚያመለክተው የሰሜን አፍሪካ ስፍራ ነው፣ ዘወትርም ግብፅንና ኩሽን የሚያመለክት (ኢሳ. 43፡3፤ 45፡14)።
የእነዚህ ስፍራ ስሞች መጠቀስ ዓላማ የቁጥር 8 እና 11ን ይዘት ለማስረገጥ ነው።

### መዝሙር ፡ 72፡12-15

[12]**ችግረኛውን ከቀማኛው እጅ፥**
**ረዳት የሌለውንም ምስኪን ያድነዋልና።**
[13]**ለችግረኛና ለምስኪን ይራራል፥**
**የችግረኞችንም ነፍስ ያድናል።**
[14]**ከግፍና ከጭንቀት ነፍሳቸውን ያድናል**
**ስማቸው በፊቱ ክቡር ነው።**
[15]**እርሱ ይኖራል ከዓረብም ወርቅ ይሰጡታል**

**ሁልጊዜም ወደ እርሱ ይጸልያሉ፥**
**ዘወትርም ይባርኩታል።**

**72፡12-15** ቁጥር 12-14 ያልተጠናቀቁት የሚሲሑን አገዛዝ ባሕርይ ይዘዋል (በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ ሳይውሉ)። ሆኖም፣ ቁጥር 15 ላይ አአመመቅ ወደ አልተጠናቀቁት ይመለሳል፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉት።

በእግዚአብሔር ሕዝብ ስሞችና ባሕርያት ላይ ያለውን ልዩነት ተገንዘብ (ዝኪ. ቁ. 2-4)።

1. ችግረኛ፣ ቁ. 12
2. ምስኪን፣ ቁ. 12
3. ደሀ፣ ቁ. 13
4. ችግረኛ፣ ቁ. 13

ቁጥር 4 ጠላቶቻቸውን "ግፈኛ፣" ብሎ እንደሰየመ፣ እዚህ እነርሱ የሚገለጹት "ግፈኞች" እና "ዓመጸኞች" በሚል ነው። እነዚህን ሰዎች መዝሙር ላይ ለመግለጽ (ለመለየት) አስቸጋሪ ነው።

1. ያልታመኑ እስራኤላውያን
2. ጣዖት አምላኪ ጎረቤቶች
3. የባዕዳን ወራሪዎች

መሲሐዊው ንጉሥ

1. ችግረኛና ምስኪኑን ያድናል
2. ለድሀና ለችግረኛ ይራራል
3. የችግረኛን ሕይወት ይታደጋል (መዝ. 69፡18)
4. የኪዳኑን ሕዝብ ከግፈኛና ከዓመጸኛ ያድናል
5. የእነርሱ ደም/ሕይወት በፊቱ የከበረ ነው (መዝ. 116፡15)

**72፡14 "ደማቸው በፊቱ የከበረ ነው"** መሲሁ "ከግፈኛ" ጋር በተቃርኖ ተመልክቷል (ዝኪ. ቁ. 4)። እሱ ለድሃ፣ ለችግረኛና ለምስኪን በቅንነት ይጠነቀቃል (መዝ. 116፡15)። እሱ የፈጣሪ ልብ አለው (ዘፍ. 1፡26፣27)! ሰዎች ሁሉ ለእርሱ ጠቃሚዎች ናቸው!

**72፡15** ይህ ቁጥር ሁለት ነጥቦች አሉት።

1. ቀዳሚዎቹ ሁለቱ ግሦች ከመሲሐዊው ንጉሥ ጋር ይዛመዳሉ
   ሀ. ይኖራል – ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ *ቃል* ተጽዕኗዊ
   ለ. ስጦታም ይሰጠዋል – ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ቀጣዮቹ ሁለቱ ግሦች ከእርሱ ሕዝብ ጋር ይዛመዳሉ
   ሀ. ሁልጊዜም ስለ እርሱ ይጸልያሉ – ቢዲቢ 813፣ ኬቢ 933፣ *ሂዝፔል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   ለ. ዘወትርም ይባርኩታል – ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ *ፒል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

ቁጥር 15ሀ የተለመደ ንጉሣዊ ገለጻ መያዙ ግልጽ ነው (ማለትም፣ "ንጉሥ ዘላለም ይኑር")፣ ነገር ግን አዲስ ፍች ይወስዳል፣ ከአኪ መገለጥ አኳያ፣ ከመሲሑ ሥጋ መልበስ እና በድል ወደ ኢየሩሳሌም መግባት ጋር!

## መዝሙር ፡ 72፡16-17

**[16]በምድር ውስጥ በተራሮች ላይ መጠጊያ ይሆናል**
**ፍሬውም ከሊባኖስ ይልቅ ከፍ ከፍ ይላል**
**እንደ ምድር ሣር በከተማ ይበቅላል።**
**[17]ስሙ ለዘላለም ቡሩክ ይሆናል፥**
**ከፀሐይም አስቀድሞ ስሙ ይኖራል**
**የምድር አሕዛብ ሁሉ በእርሱ ይባረካሉም**
**አሕዛብ ሁሉ ያመሰግኑታል።**

**72፡16-17** ሁለቱም ቁጥር 16 እና 17 የሚጀምሩት በተጽዕኗዊ ግሥ ነው፣ ይኸውም ዐውደ-ጽሑፉ ያልተጠናቀቁትን ግሦች እንደ ተጽዕኗዊ ፍቺ እንዲመለከት የሚያስችሉት፣ በእነዚህ ሁለት ቁጥሮች።

ይህ አንዳ ይቀጥላል፣ ቁጥር 3፣5-6 ላይ የተጀመረውን የበረከት ጭብጥ። ይህ በረከት የሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30 ኪዳናዊ ተስፋ ነው።

ቁጥር 17 የሚያተኩረው በመሲሑ አገዛዝ ላይ ነው።

1. ስሙ ለዘላለም ይኖራል — ለያህዌ ጥቅም ላይ የዋለ መዝ. 135፡13
2. ስሙ እንደ ፀሐይ ዕድሜ ይጨምር (ዝኪ. 72፡5-7)፤ "ይጨምር" የሚለው ግሥ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ (ቢዲቢ 630፣ ኬቢ 696፣ ኒዶቲ፣ ቅጽ. 3፣ ገጽ. 1161)፤ LXX "ይኑር" የሚል አለው፣ ከቁጥር 17ሀ ትይዩ
3. ሰዎች በእርሱ ራሳቸውን ይባርኩ (ማለትም፣ የዘፍ. 12:3፤ 22:18 ጠቃሽ ነው፤ የአብርሃማዊው ኪዳን፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 2 መግቢያ ላይ
4. አሕዛብ ሁሉ የተባረከ ይበሉት (ከቁ. 3 ጋር ትይዩ)

**መዝሙር ፡ 72፡18-19**

[18]**ብቻውን ተአምራትን የሚያደርግ**
**የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ።**
[19]**የምስጋናው ስም ለዓለምና ለዘላለም ይባረክ**
**ምስጋናውም ምድርን ሁሉ ይምላ።**
**ይሁን ይሁን።**

**72፡18-19** ቁጥር 17 (ስለ መሲሑ) ከቁጥር 18 ጋር (ስለ እስራኤል የኪዳን አምላክ) እንዴት ትይዩ እንደሆነ ተገንዘብ። ንጉሡ፣ ብሎም መሲሑ፣ የያህዌ ባሕርይ ነጸብራቅ ነው።

ሁለንተናዊውን ይዘት በድጋሚ ቁጥር 19ለ ላይ ተገንዘብ (ዘኁ. 14:21፤ ኢሳ. 6:3)።

**72፡18 "ተአምራትን ያደርጋል"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 9፡1 ላይ።

**72፡19 "አሜን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝሙር 41፡13 ላይ።

**መዝሙር ፡ 72፡20**

[20]**የእሴይ ልጅ የዳዊት መዝሙር ተፈጸመ።**

**72፡20** ይህ የአዘጋጅ ማስታወሻ ነው፣ የመዝሙርን ሁለተኛ መጽሐፍ መዝጊያ የሚያሳይ። ሊሆን የሚችለው ቁጥር 18-19 የውዳሴ መዝጊያ ነው (ዝከ. 41:13፤ 89:52) ለሙሉው ሁለተኛ መጽሐፍ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት _መመሪያ_ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ስለ ሰሎሞን ነው ወይስ ስለመፃዒው መሲሕ?
2. የሰሎሞን አገዛዝ ከቁጥር 8 ጋር ይገጥማልን?
3. እነዚህ የብኪ ቅዱስ ቃላት፣ ስለ እስራኤል አሕዛብን ሁሉ ገዥነት፣ ከአኪ ጋር እንዴት ይገጥማሉ?
4. "ምስኪን" ማንን ይወክላል?
5. ቁጥር 16 ከዘፍጥረት 12 ጋር ጋር እንደምን ይዛመዳል?
6. ቁጥር 18-19፣20 የዚህ መዝሙር አካል ነው ወይስ የመጽሐፍ II መዝጊያ?

# መዝሙር 73
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የኃጢአተኛ መጨረሻ ከጻድቅ ጋር በተጻራሪው<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የአሳፍ መዝሙር | የኃጢአተኛ አሳዛኝ ፍጻሜ እና በእግዚአብሔር የታመነው መባረክ | የእግዚአብሔርን ፍርድ ማሰላሰል | የእግዚአብሔር ፍርድ | የፍርድ ድል ነሽነት |
| 73:1-9 | 73:1-3 | 73:1-3 | 73:1-3 | 73:1 |
| | | | | 73:2-3 |
| | 73:4-9 | 73:4-9 | 73:4-14 | 73:4-5 |
| | | | | 73:6-7 |
| | | | | 73:8-9 |
| 73:10-14 | 73:10-14 | 73:10-14 | | 73:10-12 |
| | | | | 73:13 |
| | | | | 73:14-15 |
| 73:15-20 | 73:15-17 | 73:15-20 | 73:15-17 | |
| | | | | 73:16-18 |
| | 73:18-20 | | 73:18-20 | |
| | | | | 73:19-20 |
| 73:21-24 | 73:21-24 | 73:21-26 | 73:21-26 | 73:21-22 |
| | | | | 73:23-24 |
| 73:25-28 | 73:25-26 | | | 73:25-26 |
| | 73:27-28 | 73:27-28 | 73:27-28 | 73:27-28 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. አሳፍ አንደኛው የሌዋውያን የመዘምራን አለቃ ነው፣ በዳዊት ሥር (1 ዜና. 25፡1-9)።

ለ. ይህ መዝሙር የሚናገረው ባጠቃላይ የኃጢአተኛ ብልጽግና ፍትሐዊ አለመሆኑን እና ስለ ጻድቅ መከራ መቀበል ነው። እሱም ችግሩን የሚይዘው የእግዚአብሔርን ፍርድ በመጻዒው ከዚህ ሕይወት በኋላ በማመላከት ነው።

ሐ. መዝሙሩ ባህላዊውን አተያይ ያዳብራል ያስፋፋልም ("ሁለቱ መንገዶች") ሕይወትን በተመለከተ፤ ዘዳግም 27-28፤ 30:15-20፤ መዝሙር 1፤ ምሳ. 4:10-18፤ ማቴ. 7:13-14 አነጻጽር። ሕይወት ፍትሐዊ አይደለም፣ እግዚአብሔር ግን ያስተካክለዋል!

መ. መጽሐፈ ኢዮብ እና መዝሙር 37 ተመሳሳይ ችግርን ይመለከታል። ግን በዚህ ሕይወት፤ መዝሙር 73 የሚመለከተው በማቴዎስ 25 አኳያ ነው።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 73፡1-9**

**1ልባቸው ለቀና**
**ለእስራኤል እግዚአብሔር እንዴት ቸር ነው።**
**2እኔ ግን እግሮቼ ሊሰናከሉ፥**
**አረማመዴም ሊወድቅ ትንሽ ቀረ።**
**3የኃጢአተኞችን ሰላም አይቼ**
**በዓመፀኞች ቀንቼ ነበርና።**
**4ለሞታቸው መጣጣር የለውምና**
**ኃይላቸውም ጠንካራ ነውና።**
**5እንደ ሰው በድካም አልሆኑም፥**
**ከሰው ጋርም አልተገረፉም።**
**6ስለዚህ ትዕቢት ያዛቸው**
**ኃጢአትንና በደልን ተጐናጸፉአት።**
**7ዓይናቸው ስብ ስለ ሆነ ወጣ**
**ልባቸውም ከምኞታቸው ይልቅ አገኘ።**
**8አሰበው ክፉ ነገርን ተናገሩ።**
**ከፍ ከፍ ብለውም በዓመፃ ተናገሩ።**
**9አፋቸውን በሰማይ አኖሩ፥**
**አንደበታቸውም በምድር ውስጥ ተመላለሰ።**

**73፡1 "ለእስራኤል እግዚአብሔር እንዴት ቸር ነው።"** "ደግ" (ቢ.ዲ.ቢ. 373 II፣ ቁ. 9) ፍችው "ቸርነት" ነው (መዝ. 86:5፤ 145:9፤ ሰቆ. 3:25)። ይህ የመዝሙር ማጠቃለያ ነው ብሎም የብኪ መሠረታዊ ሐሳብ፣ ነገር ግን በእስራኤል ሁሉም ሰው እምነት ያለው አይደለም (ሮሜ 9-11)። ለቤተ ክርስቲያንም በተመሳሳይ ሊባል ይችላል (ማቴዎስ 7፤ 13)። ያልተለመደው የመዝ. 73፡15 ሐረግ እውነተኛውን፣ ታማኙን እስራኤልን ሊያንጸባርቅ ይችላል።

የታከሉትን ፍችዎች ተመልከት፣ ለእግዚአብሔር "ቸርነት።"

1. እሱ ለሁሉም መልካም ነው (መዝ. 45:9)
2. መልካምነቱ በቀዳሚነት የሚሆነው ስሙን በሚጠሩት ላይ ነው (መዝ. 86:5)
3. እሱ መልካም ነው፣ እርሱ ራሱ (ዕዝራ 3:11፤መዝ. 100:5፤ 106:1፤ 107:1፤ 118:1፣29፤ 136:1፤ ኤር. 33:11፤ ናሆ. 1:7)

የእስራኤል በረከት የተመሠረተው

1. በእግዚአብሔር ዘላለማዊ የመዋጀት ዓላማ፣ ለአብርሃም ዘር (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)
2. የተከታዮቹ የእምነት ግንኙነትና የኪዳን ታዛዥነት
3. የአጭር ጊዜ ሥጋዊ በረከቶች (ሮሜ 8፡18-25) ከረጅም ጊዜው ግላዊ ግንኙነት ጋር አይነጻጸሩም (ሮሜ. 8:26-30፣31-39)! ረጅሙን አተያይ መውሰዳችሁን ርግጠኛ ሁኑ! የወዲያውኑ ሁኔታዎች ሊያስቱ ይችላሉ!

▣ **"ለእስራኤል"** አየተመቅ እና የተእመቅ፣ እንዲሁም የካቶሊኩ ቅጅ አአመቅ፣ "ለእስራኤል፣" ንአገሠ'ገ የሚለውን (ቢ.ዲ.ቢ. 975) "ለእግዚአብሔር ቅን ለሆነው፣" ገሠ'ገገአ ወደሚል ይቀይረዋል (ቢ.ዲ.ቢ. 449 በተጨማሪም ቢ.ዲ.ቢ. 42 II፣ ቁ. 6)።

▣ **"ልበ ንጹሕ"** ይህ የሚያንጸባርቀው የአንዱን ዝንባሌና የውስጥ ሐሳብ ነው (መዝ. 24:4-5፤ 51:10፤ ማቴ. 5:8)።

**73:2**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ቅርብ"** |
| **አኪጀት፣ አየተመቅ፣** | |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"የቀረበ"** |
| **አእቅ** | **"በቅርብ"** |
| **አኢመቅ** | **"ስፍራው ላይ"** |

ይህ የዕብራይስጡን ተውሳከ ግሥ ቢ.ዲ.ቢ. 589 ያንጸባርቃል። እሱም የመዝሙረኛውን እምነት መውደቅ የምርነት በግልጽ ያሳያል! እሱም ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን መተማመን፣ መታመን፣ ዋስትና፣ እና ሰላም ሊያጣ ያለበት ደረጃ መድረሱን ያሳያል። የእምነት መውደቅ በይዘቱ

1. የተስፋን መበላሸት ያስከትላል
2. የብርታትና እድገት ምንጭንም

ሁላችንም እናውቃለን ከሁለቱ አንዱን የተለማመዱትን ሰዎች እናውቃለን!

▣ **“አሰናካይ... አንሸራታች”** ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ዘይቤ ነው፣ የሕይወት ስልት። ቀጥተኛው አመቺው መንገድ ጽድቅ ነው (መዝ. 40፡2)፣ ነገር ግን ጠማማው፣ አንሸራታቹ መንገድ ኃጢአተኝነት ነው (መዝ. 73:18፤ ምሳ. 3:23)። በሕይወት ሁለቱ አማራጮች “ሁለቱ መንገዶች” የሚባሉት ናቸው (ማለትም፣ መዝሙር 1 እና ዘዳ. 30፡15-20)።

“መንሸራተት” የሚለው ቃል የተተረጎመው በጥሬው “መፍሰስ” በሚል ነው (ቢዲቢ 1049፣ ኬቢ 1629፣ ቃል ተገብሮ የተጠናቀቀ)። እዚህጋ ብቻ ነው ፍች የሚኖረው (በትይዩ ቅኔያዊ ስንኝ የተገለጸ፣ “መሰናከል” በሚለው) በራስ ስፍራ ላይ መንሸራተት።

መዝሙር 73፡3 የችግሩን አካባቢ ያብራራል (ማለትም፣ ምቀኝነት፣ ቅናት)።

**73:3 “የኃጢአተኞችን ሰላም አይቼ... በዓመፀኞች ቀንቼ ነበርና”** ይህ ዓለም ፍትሐዊ አይደለም። ያለው ይህ ዓለም ብቻ ቢሆን፣ እግዚአብሔር ፍትሐዊ አይደለም!

“ልባቸው ንጹሕ የሆነ” መዝ. 73፡1 በሕይወት ፍትሐዊ አለመሆን ተፈትነዋል። የተሰመረበት ሐሳብ፣የሚፈረድበት እንዲሆን እግዚአብሔር መፍቀዱ ነው! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር የራሱን ሰዎች ይፈትናል።

**73፡4-9** እነዚህ ቁጥሮች የሚገልጹት መዝ. 73፡3 ላይ የተጠቀሱትን ሰዎች የሕይወት ስልት ነው (ማለትም፣የኪዳኑ ማኅበረሰብ ትዕቢተኛና ባለጠጋ፣ ኃጢአተኛ ሰዎች)።

1. ለሞታቸው መጣጣር የለውም
2. አመጋገባቸው ደኅና ነው፣ መዝ. 73፡4ለ፣ 7ሀ
3. በውጭ የሚታይ ችግር የለባቸውም
4. ትዕቢት ያዛቸው፣ መዝ. 73፡6ሀ፣ 8ለ
5. በዓመጻ ያደርጋሉ፣ ያለ ፍርድ
6. ክፉ አሳቢዎችና ሐሜተኞች
7. ክፉ ሥራቸውን በኩራት ያደርጋሉ፣ በእግዚአብሔር ፊት እንኳ፣ መዝ. 73፡11

ከብኪ ሥነ-መለኮት (ማለትም፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30) ብልጽግና ከእግዚአብሔር የሆነ በረከት ነው፣ ለእምነትና ለታዛዥነት (መዝ. 73፡10)፣ እነዚህ ሰዎች ግን እነዚያን ጽሑፎች መቀለጃ አድርገዋቸዋል!

**73:4 “ለሞታቸው መጣጣር የለውምና”** ይህም (1) ማዕርግ ያለው ቀብር ይደረግላቸዋል ወይም (2) ሞታቸው ፈጣንና ሥቃይ-የለሽ ነው ማለት ነው።

▣ ***“ሥቃይ” ይህ*** የዕብራይስጥ ቃል (ቢዲቢ 359) ሁለት ጊዜ ብቻ ነው ብኪ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው፣ እጅግ በተለያዩ መልኮች።

1. “እግር-ብረት” ወይም “እስራት” — 58፡6 (ነጠላ ቁጥር)
2. “ሥቃይ” — መዝ. 73፡4 (የብዙ ቁጥር)

አእት መጽሐፍ ቅዱስ የሚለው፡

“እሱም ከዘይቤአዊነት አኳያ ለሥቃይ እና መከራን መቀበል ይውላል፣ የአንዱን የሕይወት ደስታ የሚያግድ” ገጽ 941)።

ቲንዳሌ ሐተታ በዴሪክ ኪድነር (ገጽ 289፣ የግርጌ ማስታወሻ ቁ. 2) ከየተመቅ ጋር ይሰማማል፣ “በሞታቸው” בְּמוֹתָם፣ የሚለውን ወደ ሁለት ቃላት לָמוֹ תָּם በመቀየር፣ በውጤቱም “ምንም መጣጣር ለእነርሱ የለባቸውም፣ አካላቸው በደኅንነትና በመልካም ሁኔታ ነው።” ይህም በአየተመቅ እና የተእመቅ ይከተላል።

▣ **“ሰውነታቸው ሰብቷል”** እነርሱ ሕመም የነካቸው አይመስሉም፣ ወይም የተለመዱት የሕይወት ችግሮች (ማለትም፣ ጤነኛ አካል፤ የዕብራይስጡ ቃል [ቢዲቢ 17 I]) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው።

**73:5**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **“እንደ ሌሎች ሰዎች በችግር አልሆኑም”** |
| **አኢመቅ** | **“የሰዎች ዕጣ ከሆነው ችግር ተትተዋል”** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **“በሰዎች ላይ የሚደርስ ችግር አያገኛቸውም”** |

ክፉዎች ከሕይወት የተለመዱ ችግሮች የተጠበቁ ይመስላሉ። ይህ በቅድሚያ፣ የእግዚአብሔር ድርጊት ይመስላል። ይህ ሥነ-መለኮታዊ ችግር ነው፣ “ከሁለቱ መንገዶች” ጋር በተያያዘ (ኢዮብ፤ መዝሙር 73)።

▣ **“ቅጣት”** ይህ ቃል (ቢዲቢ 619፣ ኬቢ 668፣ ፑኣል ያልተጠናቀቀ) ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለመለኮታዊ ቅጣት ነው (ዘፍ. 12:17፤ 2 ነገ. 15:5፤ 2 ዜና. 26:20፤ ኢሳ. 26:5፤ ኢዮብ 1:11፤ 2:5)። እሱም የሚመስለው የእግዚአብሔር የራሱ ቃላት (ማለትም፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30፤ መዝሙር 1) ስለ ክፉ የተባሉት እንዳልሆነ ነው። መዝ. 73፡14 ላይ ተመሳሳይ ቃል ጥቅም ላይ ውሏል፣ ለመዝሙረኛው የአእምሮ ኀዘን፣ በገዛ ራሱ ጥርጣሬ የተፈጠረ።

**73:6** ከሕይወት ልምዳቸው የተነሣ (መዝ. 73፡4-5) ትዕቢተኛ፣ ባለጠጋ፣ ኪዳን አፍራሾች በግልጽ ይኖራሉ፣ በማስመሰልም ጭምር፣ መልካም ያልሆነ ሕይወታቸውን (መዝ. 73፡6-9)።

**73:7**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“ዓይናቸው ስብ ስለ ሆነ ወጣ”** |
| **አእቅ** | **“ልባቸውም ክፉ ነገርን አፈለቀ”** |
| **አኢመቅ** | **“ከስባቸው ክፋት ወጣ”** |
| **LXX** | **“ፍትሕ አልባነታቸው ከስብ እንደወጣ ዓይነት ይሄዳል”** |
| **ፔሺታ** | **“በደለኝነታቸው ይወጣል እንደ ስብ ቅባት”** |

**ጀፒኤስኦኤ** **"ዓይናቸው በስብ ተሸፍኗል"**

"በደለኝነት" የሚለው ሐሳብ ከLXX፣ ሶርያ፣ ፔሺታ፣ እና ቫልጌት የተተረጎመ ነው። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 314) "ዓይናቸው" ለሚለው "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል (ማለትም፣ ሁነኛ ጥርጣሬ)።

"በደል" עובמו ነው

"ዓይናቸው" עיבמו ነው

"ዓይኖች" ከመዝ. 73፡7 ዐውደ-ጽሑፍና ትይዩነት ጋር በተሻለ ይደጥማል።

**73:8 "መቀለድ"** ይህ ባጠቃላይ የዓረብኛ ቃል (ቢዲቢ 558፣ ኬቢ 559) እዚህጋ ብቻ ነው ነው የሚከሰተው፣ ብኪ ላይ።

---

## መዝሙር ፡ 73፡10-14

**10 ስለዚህ ሕዝቤ ወደዚህ ይመለሳሉ**
**ፍጹም ጊዜም በላያቸው ይገኛል**
**11 እግዚአብሔር እንዴት ያውቃል?**
**በልዑልስ ዘንድ በውኑ እውቀት አለ? ይላሉ።**
**12 እነሆ፥ እነዚህ ኃጢአተኞች ይደሰታሉ፥**
**ሁልጊዜም ባለጠግነታቸውን ያበዛሉ።**
**13 እንዲህም አልሁ። በውኑ ልቤን በከንቱ አጸደቅሁ፥**
**እጆቼንም በንጽሕና በከንቱ አጠብሁ።**
**14 ሁልጊዜም የተገረፍሁ ሆንሁ፥**
**መሰደቤም በማለዳ ነው።**

---

**73፡10** ይህ ቁጥር በኤምቲ ርግጠኛ አይደለም። የዐውደ-ጽሑፉ ፍሰት የሚያሳየው

1. ክፉ ሰዎች በአዎንታዊነት ሌሎች የኪዳን ሰዎች ላይ ተጽዕኖ አሳርፈዋል (የካቶሊክ ባህል ሲሲዲ የሚያስበው መዝ. 73፡10 ከክፉ እስራኤላውያን የተጠቀሰ ነው)
2. ክፉዎች መልካሙን ነገር ሁሉ ለራሳቸው ያግበሰብሳሉ
3. የክፉዎች ተከታዮች እነሱ ያሉትን ሁሉንም ነገር ያምናሉ (ኒዶቲ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 1065)

በመሠረቱ ይህ የመዝሙረኛው ግራ መጋባት ነው። እሱ ያየው ትዕቢተኛ፣ ተሳዳቢ፣ የኪዳን ሰው ሁሉንም የኪዳን ጥቃሞቶችና በረከቶች ሲቀበሉ ነው! በዚህ ምክንያት ነው ጥያቄ የሚጠይቀው፣ የመዝ. 73፡13ን! "እንዲህ ከሆነ... ከዚያም" የሚለው የሙሴአዊ ኪዳን (ማለትም፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30) ምንም ውጤት ያለው አይመስልም። ምድር "ከላይ ወደ ታች የተገለባበጠ" ይመስላል።

ኤቢ፣ አእት መጽሐፍ ቅዱስን ተከትሎ የሚለው የመጀመሪያው ስንኝ ማሻሻያ እንደሆነ ነው። እነርሱ "ሕዝቡን መልሶ ያመጣቸዋል" (ኤም ቲ) የሚለውን ወደ "ምግብን ይጠግባሉ፣" ቀይረውታል፣ እሱም ለቀጣዩ ስንኝ የተሻለ ትይዩ የሆነ።

**73:11 "እግዚአብሔር እንዴት ሊያውቅ ይችላል?"** ኃጢአተኛ ግልጽ የሆነ ትዕቢትንና ስድብን በያህዌ ላይ ያሳያል (መዝ. 73፡9)።

የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ አስደናቂ ጥቅስ አለው (ገጽ 1362)።

> "በጥንቶቹ ጊዜያት ምንም አምላክ-የለሽነት አልነበረም፣ እግዚአብሔርን ያለማወቅ አሻሚ ሐሳብና ኃይል የለሽነት ብቻ እንጂ" (መዝ. 10:4፣11፣13፤ 94:7)።

ይህ ዓይነቱ የቅድመ-እውቀት ማነስ ማስረገጫ በዘመናዊው "ኦፐን ሲዝም" ሥነ-መለኮት ዳግም ይከሰታል። እኔ በግሌ የማስበው ይህ ሥነ-መለኮት የብኪን ጽሑፋዊ ብልሃት እንደ ወሰደ ነው (ማለትም፣ እግዚአብሔር ጥያቄዎችን ሲጠይቅ፣ ዘፍ. 3፡9) እሱንም ይዞ ሁሉንም የመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፎች ማጣሪያ ፈርጅ አድርጎ መጠቀም። እሱም ተሻሽሎ "የተሻሻለው ሲዝም" መልክ ይዟል፣ ከአልፍሬድ ኖርዝ ዋይትሄድ።

▣ **"ልዑሉ"** ይህ የዕብራይስጥ መጠሪያ ኤሊዮን ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች)። እሱም ዘፍጥረት 14 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል (ማለትም፣ የመልከጼዴቅ ስም ለመለኮት) አራት ጊዜ፣ እና ሃያ አንድ ጊዜ መዝሙር ላይ፣ ስድስት ጊዜ ብቻ በቀሪው ብኪ ላይ።

**73:13 "በውኑ ልቤን በከንቱ አጸደቅሁ፥"** ይህ የመዝሙረኛውን ጥርጣሬ ያንጸባርቃል፣ ስለ እግዚአብሔር መልካምነትና ፍትሐዊነት፣ "ከችግሬ" አዝማሚያ ጋር ተደበላልቆ። ይህ ከሞላ ጎደል የሚያንጸባርቀው "ለእኔ ምን ይኖረዋል" ከሚለው አዝማሚያ ጋር ነው (ኢዮብ 1፡6-12)።

ይህ ከሥነ-መለኮት አኳያ ሰይጣን ኢዮብን ከከሰሰው ጋር የሚመሳሰል ነው፣ እሱ እግዚአብሔርን የሚያገለግለው እግዚአብሔር ስለ ባረከውና ስለ ጠበቀው ነው ከሚለው ጋር (ማለትም፣ ስለ ሞገስ እምነት)።

የብኪ "ሁለቱ መንገዶች" የተገላቢጦሽ የሆኑ ይመስላል! ይህም ስፍራ ነው "ታማኝ ተከታዮች" ማስታወስ የሚኖርባቸው፣ በወደቀ ዓለም እንደምንኖር። ይህ ዓለም እግዚአብሔር እንዲሆን የፈለገው አይደለም። የብኪ ዓላማ ለሰዎች ዓመጸኝነታቸውንና ኃጢአተኝነታቸውን ማሳየት ነበር (ገላትያ 3)!

መልካምነትና ታማኝነት መሳለቅንና መናቅን ከወደቀው ዓለም ያመጣል (ማቴ. 5:10-16)፣ ነገር ግን አዲስ ቀን እየመጣ ነው (ኤር. 31:31-34፤ ሕዝ. 36:22-38)።

▣ **"በርግጥ"** ይህ ተውሳከ ግሥ (ቢዲቢ 36)፣ ለ "ጥርጣሬ" በመዝ. 73:13 ጥቅም ላይ የዋለው ፣ መዝሙር መዝ. 73:18 ላይ ማስረገጫ ሆኗል! መዝሙረኛው የጽድቅ ሕይወትን በከንቱ አልኖረም፣ እናም ኃጥአን የዘሩትን ያጭዳሉ (ኢዮብ 34:11፤ መዝ. 28:4፤ 62:12፤ ምሳ. 24:12፤ መክ. 12:14፤ ኤር. 17:10፤ 32:19፣ ለአኪ ጽሑፎች የተሟላ ዝርዝር ገላ. 6:7 ዌብ ሳይት መስመር)።

▣ **" እጆቼንም በንጽሕና አጠብሁ።"** ይህ ትርጉም በርግጥ ይቻላል፣

1. ኤምቲ መግቢያ መዝሙር 73
2. የሌዋውያን ምናባዊ ምስያ
3. "ዕጣ ፈንታ" በሚለው የመሥዋዕታዊ ቃል መዝ. 73፡26 ላይ በመመሥረት
ደራሲው ሌዋዊ ወይም ካህን ሊሆን ይችላል። እጅ መታጠብ የቤተ መቅደስ የአምልኮ ሥርዓት አካል ነበር።
ሆኖም፣ ፈሊጡ ሰፋ ያለ ፍች ይወስዳል "መልካም አኗኗር" (ዘዳ. 21:6፤መዝ. 26:6)፤ ደግሞም የዘፍ. 20:5ን ፈሊጥ ተመልከት።

**73፡14** "ቀኑን ሁሉ" በሚለው እና "በየማለዳው" በሚለው መካከል ትይዩነት አለ፣ ሁለቱም የተራዘመ ጊዜና ሰዓት ፈሊጦች በመሆናቸው (ማለትም፣ የሕይወት ዘመን)። መዝሙረኛው የታማኝነት ሕይወት መኖሩን እያስረገጠ ነው።

የሐረጉ ተገብሮ ድምጸት "የተገረፍኩ ሆንኩ" (ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ ቃል ያልተጠናቀቀ ከቢዲቢ 619፣ ኬቢ 668፣ ቃል ተገብሮ አንቀጽ ጋር ተደባልቆ) የሚያመለክተው እግዚአብሔር የኃጢአተኞችን ድርጊት እና ሐሳብ  መፍቀዱን ወይም ችላ ማለቱን ብቻ አይደለም፣ ግን ለታማኝ መዝሙረኛው በትዕቢተኛ፣ ተሳዳቢ፣ ያልታመነ የኪዳን ጓደኛ ላይ መደረግ ያለበትን ማድረጉ እንጂ! ይህ የሁነቶች ምሥጢር ነው በወደቀው ዓለም። ይህ ዓለም እግዚአብሔር እንዲሆን የፈለገው አይደለም። ከእግዚአብሔር ያልሆኑ ነገሮች ይሆናሉ። ብኪ ላይ አሀዳዊነትን ለማጽናት አንድ ምክንያታዊነት ብቻ አለ (መክ. 7:14፤ ኢሳ. 45:7፤ ዐሞጽ 3:6) ነገር ግን ቀጣይነት ካለው መገለጥ ጉዳዩ ያ እንዳልሆነ እንረዳለን። እግዚአብሔር ይፈቅዳል የተወደደ ፍጡሩ የዘፍጥረት 3ን የከፋ ውጤት ያጭድ ዘንድ። መልካሙ ዜና

1. እሱ በመጨረሻ ጊዜውን ይወስነዋል (ማለትም፣ አዲሱ ዘመን)
2. እሱ ከእኛ ጋር ነው፣ በመካከሉ ላይ (መዝሙር 23)

**መዝሙር ፡ 73፡15-20**

**15እንደዚህ ብዬ ብናገር ኖሮ፥**
**እነሆ፥ የልጆችህን ትውልድ በበደልሁ ነበር።**
**16አውቅም ዘንድ አሰብሁ፥**
**ይህ ግን በፊቴ ችግር ነበረ።**
**17ወደ እግዚአብሔር መቅደስ እስክገባ ድረስ፥**
**ፍጻሜአቸውንም እስካስተውል ድረስ።**
**18በድጥ ስፍራ አስቀመጥኻቸው፥**
**ወደ ጥፋትም ጣልኻቸው።**
**19እንዴት ለጥፋት ሆኑ!**
**በድንገት አለቁ ስለ ኃጢአታቸውም ጠፉ።**
**20ከሕልም እንደሚነቃ፥**
**አቤቱ፥ ስትነቃ ምልክታቸውን ታስነውራለህ።**

**73፡15-20** ይህ አንጓ የዚህ መዝሙር ሥነ-መለኮታዊ ልብ (ዋና ነገር) ነው። ዋነኞቹን ነጥቦች ተገንዘብ።

1. ታማኝ ተከታዮች በግልጽ ጥርጣሬያቸውንና መደናገራቸውን ሲገልጹ በሌሎች አማኞች ላይ ተጽዕኗቸውን ሊያሳርፉ ይችላሉ።
2. ከእግዚአብሔር ጋር ለሚሆን ኅብረት ስፍራና ጊዜ በተደነጋገርንበት ነገር ላይ ሰላምን ሊያመጣ ይችላል።
3. የኃጢአተኞች ብልጽግና ለአጭር ጊዜ ነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ፊት ለፊት የሚቀርቡበት ጊዜ በርግጥ ይመጣል (መዝ. 73፡27)።

ይህም ማረጋገጫነቱ "ሁለቱ መንገዶች" ገና ዋጋ እንዳላቸው ነው! የዘራነውን እናጭዳለን!

**73፡16 "ይሄንን አውቅ ዘንድ ሳስብ"** የእግዚአብሔርን መንገድ የመረዳት አቅማችን፣ በወደቀው፣ በምድራዊው፣ በጊዜ በተወሰነው የሰው እውቀት ወደ ውድቀት ያደርሳል (ምሳ. 3:5ለ፤ ኢሳ. 55:8-13፤ ቆላ. 2:8)። እውቀት መልካም ነው፣ መታመን ግን ይሻላል!

**73፡17 "ወደ መቅደስ እስክገባ ድረስ"** "መቅደስ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 874) የብዙ ቁጥር ነው፣ እሱም ሞላውን የመቅደስ አካባቢ የሚገልጽ ወይም የግርማውን ብዙኅነት። አምልኮ መዝሙረኛውን ረድቶታል በግልጽ ያይ ዘንድ። በትግሉ ሰዓት ይሄንን ችላ ያለው ይመስላል።

▣ **"ፍጻሜአቸውንም እስካስተውል ድረስ።"** መገለጥ መጥቷል ዓይኖቹም ለትልቁ ምስል ተከፍተዋል— እሱም አርቆ አየ፣ ሁለቱንም በጊዜውም ሆነ ከጊዜው ባለፈ።

**73፡18-20** የዓመጸኝነት ውጤቱ አስፈሪ ሞት ብቻ አይደለም፣ ግን ደግሞ አስፈሪ ዘላለማዊነት እንጂ (ማቴ. 25:31-46፤ ሉቃስ 16:19-31፤ ራዕ. 20:11-15)።

**73፡19** "ጥፋት" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 117) የሚያመለክተው ሞትን ነው (ኢዮብ 18:11፣14)። ኤቢ መዝሙር ላይ፣ በሚትቼል ዳሆድ በርካታ የዕብራይስጥ ቃላትንና ፈሊጦችን አግኝቷል፣ ከኡጋሬት አጠቃቀም የተነሣ ከምድር በታች ላለ ምስያ የሚሆን።

**73:20 "ሲነቃ"** መስተጻምሩና ግሡ (עיר ፣ ቢዲቢ 734፣ ኬቢ 802፣ ሂፊል ያልተወሰነ አወቃቀር) ታርሟል (LXX፣ ፔሺታ፣ ቫልጌት) ወደ "ከተማ" (עיר ፣ ቢዲቢ 746 II)። ይህም የሚያመለክተው

1. "የመናፍስት ከተማ" (ኤቢ፣ ማለትም፣ ሲኦል)
2. የኢየሩሳሌም ማጣቀሻ (ማለትም፣ እነርሱም በእግዚአብሔር መገኘት አልተካተቱም፣ በኃጢአት እና/ወይም ስደት)

የእግዚአብሔር ከእንቅልፍ መንቃት ወይም ለሥራ ከዙፋኑ መነሣት ጽንሰ-ሐሳብ በብኪ ጥቅም ላይ የሚውለው እንደ ዘይቤአዊ ቋንቋ ነው፣ ለመለኮት ግልጽ የሆነ አለመሥራት ምሥጢር ወይም/እና ለምድራዊ ሁነቶች ፍትሐዊ አለመሆን እንዲሆን ነው። እግዚአብሔር ራሱን ገልጧል ነገር ግን የእርሱ ተስፋዎችና የሰዎች ሁኔታ ለምን የተለዩ ሊሆኑ ቻሉ?

▣
**ኢአመመቅ** **"ምስል"**
**አኪጀቅ፣ አኢመቅ፣**
**ጀፒኤስኡኤ** **"ምስል"**
**አየተመቅ፣ LXX** **"መናፍስት"**
**ፔሺታ** **"ጣዖት ማምለክ"**

ይህ ቃል (ቢዲቢ 853) ሁለቴ ብቻ ነው ብኪ ላይ የሚከሰተው (እዚህጋና መዝ. 39:6 ላይ)። ኒዶቲ፣ ቅጽ. 3፣ ገጽ. 810፣ የሚለው እሱ የሚገልጸው ምስልን ወይም ጥላን ነው። እሱም የመጣው ከጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ሥር "ጨለማ፣" "ጥቁር" ነው (ሌለኛው መልክ የሚሆነው "በሞት ጥላ ሸለቆ፣" መዝ. 23፡4)።

**መዝሙር ፡ 73፡21-24**

**21ልቤ ነድዶአልና፥**
**ኵላሊቴም ቀልጦአልና**
**22እኔ የተናቅሁ ነኝ አላውቅሁምም፥**
**በአንተ ዘንድም እንደ እንስሳ ሆንሁ።**
**23እኔ ግን ዘወትር ከአንተ ጋር ነኝ፥**
**ቀኝ እጄንም ያዝኸኝ።**
**24በአንተ ምክር መራኸኝ**
**ከክብር ጋር ተቀበልኸኝ።**

**73፡21 "በውስጥ"** ይህ በጥሬው "ኵላሊቶች" ነው (ቢዲቢ 480)። ዕብራይስጡ የሚያመለክተው የሆድን ታችኛ ክፍል ነው፣ የስሜት መኖርያ (ኢዮብ 19:27፤ ምሳ. 23:16) እና የአእምሮ እንቅስቃሴ (ተግባር) (መዝ. 16:7)።

**73፡22** እንሰሳት ምንም የሞራል ስሜት የላቸውም። ሰዎች ናቸው በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠሩት (ማለትም፣ ዘፍ. 1፡26-27)። እነርሱ ብቻ ናቸው የሞራል ስሜት ያላቸው። መልካሙንና ክፉውን የማወቁ ዛፍ በዔድን ገነት ይሄንን የሞራል ግራ መጋባት አጽንዖት ሰጠው (ዘፍ. 3፡8-13)። አንዱን "አውሬ" ብሎ መጥራት ፍችው ምንም ዓይነት የሞራል አመላካች ወይም አቅጣጫ የላቸውም ማለት ነው፣ እንደ እንስሳ እንዲያው ይኖራሉ (ማለትም፣ የወዲያውኑ ፍላጎታቸውን ወይም መሻታቸውን ለማግኘት)። መዝሙረኛው ተሰምቶታል፣ ጥርጣሬውና ቅናቱ እግዚአብሔርን እንደማያውቅ እንዲሠራ እንዳደረገው (ማለትም፣ መዝ. 73፡21-22)። ሰዎች ሁሉ በእነዚህ መሰሎቹ "ተገቢ ከሆነው በታች" ስሜቶች ያልፋሉ። እውነተኛ አማኞች ከእነዚህ ጊዜያት ይወጣሉ፣ ብርቱና ርግጠኛ ወደሆነው የእግዚአብሔር ታላቅ ምሕረትና መገኘት! ሁነኛ የማይመስሉ ዝንባሌዎች ወደ ታላቅ እምነት መረማመጃ የደረጃ ድንጋዮች <u>ሊሆኑ</u> ይችላሉ!

**73፡23-24** የእግዚአብሔር በረከቶች፡

1. የእርሱ መገኘት በሕይወታችን (መዝ. 73፡28ሀ)
2. የእርሱ የየቀኑ ምሪት (ማለትም፣ የመዝሙረኛውን "ቀኝ እጅ" ይዟል)
3. የእርሱ አሁን መቀበል
4. የእርሱ መቀበል ለዘላለም (ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 73፡24 ላይ)

እምነት ወደ ኋላ በሚመለከትበት ጊዜ፣ እሱ የእግዚአብሔርን እጅ አጥርቶ ይመለከታል። ያለፈው ታማኝነትና ምሕረት ለታማኝ ተከታይ ተስፋ እና መተማመንን ይሰጠዋል፣ ለቀጣዩ የእግዚአብሔር መገኘትና ተስፋ!

**73፡24** ተርጓሚዎች ሊጠነቀቁ ይገባል፣ የአኪን መገለጦች ወደ አሻሚዎቹ የብኪ ጽሑፎች በግምታዊነት እንዳይወስዱ። የብኪ ጽሑፎች አሉ ወደ ወደፊቱ ተስፋ የሚያመለክቱ፣ አካላዊ ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር። ሆኖም፣ ይህ ጽሑፍ ከእነዛ አንዱ ሊሆን አይችልም።

1. "ክብር" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 458) ወደ ሰማይ አያመለክትም፣ ብኪ ላይ ሌላ የትም ስፍራ (ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ ገጽ 642፤ አይቪፒ ዳራ ሐተታ ገጽ 540 ተመልከት)
2. "ወደ" የሚለው መስተጻምር በጽሑፉ ላይ የለም (ምንም መስተጻምር የለም)። LXX "ከ ጋር"ን ያሳያል።
3. "ክብር" "ከበሬታን" ያሳይ ይሆናል (ጀፒኤስኡኤ፣ አየተመት፣ ፔሺታ) ከኃጢአተኛ የሆነ ይመስላል፣ ነገር ግን በእውነታው፣ ከመዝሙረኛው ጋር ነው

በሌላ በኩል

1. "መቀበል" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 542፣ ኬቢ 534፣ ቃል ያልተጠናቀቀ) ለሄኖክ ነው ጥቅም ላይ የዋለው ዘፍ. 5:24 ላይ፣ እሱም ወደ እግዚአብሔር መገኛ የተሸጋገረ፣ እንደ ኤልያስ (2 ነገ. 2:3፣10-11)
2. "ከዚያም በኋላ" የሚለው ተውሳከ ግሥ (ቢዲቢ 29) መዝ. 73:24 ላይ ይከሰታል፣ እሱም የማጠቃለያውን ሁነት የሚያሳይ የሚመስል
3. "ሰማይ" (ቢዲቢ 1029፣ ሁለት ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማይ እና ልዩ ርዕስ፡ ሰማይና ሦስተኛው ሰማይ) መዝ. 73፡25 ላይ ተጠቅሷል
4. "ዘላለም" የሚለው ቃል መዝ. 73፡26 ላይ በተቃርኖ ጥቅም ላይ ውሏል፣ "ካንተ የራቁ ይጠፋሉ" ከሚለው ጋር

የሁሉም ታማኝ ተከታዮች ተስፋ ከእግዚአብሔር ጋር ለዘላለም መሆናቸው ነው (መዝ. 23:6፤ 27:4-6)። እሱም "የየት" ጥያቄ አይደለም ነገር ግን "የማን" ጥያቄ እንጂ! ሰዎች የተፈጠሩት ከእግዚአብሔር ጋር ላለ ኅብረት ነው፤ ሌላ ምንም ለማድረግ ሳይሆን!

**መዝሙር ፡ 73፡25-28**

[25]በሰማይ ያለኝ ምንድር ነው?
በምድርስ ውስጥ ከአንተ ዘንድ ምን እሻለሁ?
[26]የልቤ አምላክ ሆይ፥ ልቤና ሥጋዬ አለቀ
እግዚአብሔር ግን ለዘላለም እድል ፈንታዬ ነው።
[27]እነሆ፥ ከአንተ የሚርቁ ይጠፋሉና
ከአንተ ርቀው የሚያመነዝሩትንም ሁሉ አጠፋኻቸው።
[28]ለእኔ ግን ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይሻለኛል
መታመኛዬም እግዚአብሔር ነው
በጽዮን ልጅ በሮች ምስጋናህን ሁሉ እናገር ዘንድ።

**73፡25 "በምድርስ ውስጥ ከአንተ ዘንድ ምን እሻለሁ?"** እግዚአብሔር ራሱ ታላቁ መሻታችን ነው! የተፈጠርነው ከእርሱ ጋር ላለ ኅብረት ነው (ዘፍ. 1:26-27፤ 3:8)።

ይህ ሐረግ ለአንዱ እውነተኛ አምላክ ያለን የኪዳን ታማኝነት ማስረገጫ ነው ማለት ይቻላል። መዝሙረኛው ያስረግጣል በጣዖት አምልኮ ፈጽሞ አለመሳተፉን ("የጋለሞታ ድርጊት፣" ማለትም፣ ማመንዘር፣መዝ. 73፡27)።

**73፡26 "እግዚአብሔር ብርታቴ ነው"** የእርሱ የሚለወጥ አለመሆን ተስፋችን ነው (መዝ. 18:1-3፤ ሚል. 3:6)።

▣ **"ለዘላለም እድል ፈንታዬ"** እግዚአብሔር ራሱ የሌዋውያን ርስት ነበር (ዘዳ. 10:9፤ 12:12፤ 14:27፣29፤ 18:1፤ መዝ. 16:5 ሰቆ. 3:24) አሁንም የታማኝ ተከታዮች ሁሉ ርስት ነው (ሐዋ. 15፤ ሮሜ. 2:28-29፤ ገላትያ 3)!

**73:27 "ያልታመኑ"** ይህ በጥሬው "ወደ አመንዝራ መሄድ" ነው (ቢዲቢ 275፣ ኬቢ 275፣ ቃል አንቀጽ)። ይህም እግዚአብሔር እንደ ባል መሆኑን የሚያሳይ ጽንሰ-ሐሳብ ነው (ሆሴዕ 1-3)። እሱን መተው መንፈሳዊ አመንዝራነት ነው (ዘጸ. 34:15፤ ዘኁ. 15:39፤ ሆሴ. 4:12፤ 9:1)።

**73:28 "መቅረብ"** ተቃርኖውን ተገንዘብ "ካንተ ርቀው ያሉትን" (መዝ. 73፡27) በሚለው እና "ወደ እግዚአብሔር መቅረብ" በሚለው መካከል ያለውን (መዝ. 73፡28)።

▣ ***"መታመኛዬም እግዚአብሔር ነው"*** የመለኮት ስም እዚህጋ ሐዶናይ ያህዌ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።
ለ "መጠጊያ" (ቢዲቢ 340) መዝ. 5፡11 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

▣ ***"ሥራህን ሁሉ እናገር ዘንድ"*** ዋነኛ ነገር ነው፣ ታማኝ ተከታዮች እግዚአብሔር ለእነርሱ ያደረገውን ነገር ለሌሎች መግለጻቸው። ይህም የመዝ. 73፡15 ተቃራኒ ነው።

አንዳንድ ሊቃውንት ይሄንን መዝሙር እንደ "ጥበብ መዝሙር፣" ይመድቡታል፣ ነገር ግን ይህ ሐረግ አንድምታው "የምስጋና መዝሙር" እንደሆነ ነው፣ የሚያሳየው። ምስጋና የማቅረብ ምስክርነት እና በመቅደስ የሚደረግ መሥዋዕት የዚህ ዓይነቱ መዝሙር ዘውግ የተለመደ ይዘት ነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "መልካም" የሚለውን ቃል በመዝ. 73፡1 ላይ ግለጽ።
2. በልብ ንጹሕ መሆን ምን ማለት ነው?
3. መዝሙረኛው በያህዌ ላይ የነበረውን እምነት/መታመን/መተማመን ለምን አጣ?
4. "ኃጢአተኛ" ተብለው መዝ. 73፡3-9 ላይ የተገለጹት እነማናቸው?
5. መዝ. 73፡13 እንዴት ከኢዮብ 1-2 የሰይጣን ክስ ጋር ትይዩ ይሆናል?
6. መዝሙረኛው ጥርጣሬውን እንዴት ሊያመልጥ ቻለ?
7. የቁጥር መዝ. 73፡23-24 ጠቀሜታዎች ዘርዝር።
8. መዝ. 73፡25-26 የሚናገረው የዚህን ሕይወት ማስረገጫ ነው ወይስ ከዚህ በኋላ የሚኖረውን? ለምን፣ ካልሆነስ ለምን?
9. መዝ. 73፡28ሀ ምን ማለት ነው?

# መዝሙር 74
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ጥያቄ ምድሪቱ በጠላት በመጥፋቷ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የአሳፍ መዝሙር | ከግፈኞች ለማረፍ ጥያቄ | ከብሔራዊ ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት | ጸሎት ለብሔራዊ መታደግ | ሰቆቃ በመቅደሱ ጥፋት |
| 74:1-11 | 74:1-8 | 74:1-3 | 74:1-3 | 74:1-2 |
| | | | | 74:3-5ሀ |
| | | 74:4-8 | 74:4-8 | |
| | | | | 74:5ለ-7 |
| | | | | 74:8-9 |
| | 74:9-17 | 74:9-11 | 74:9-11 | |
| | | | | 74:10-11 |
| 74:12-17 | | 74:12-17 | 74:12-17 | 74:12-13 |
| | | | | 74:14-15 |
| | | | | 74:16-17 |
| 74:18-21 | 74:18-21 | 74:18-19 | 74:18-19 | 74:18-19 |
| | | 74:20-23 | 74:20-21 | 74:20-21 |
| 74:22-23 | 74:22-23 | | 74:22-23 | 74:22-23 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

*ሀ.* ይህ መዝሙር ጥያቄ ነው፣ ለኪዳኑ አምላክ፣ ሕዝቡን እንዲያስታውስ (መዝ. 74:1፣18፣22)፣ የተስፋይቱ ምድር (ዘፍ. 12፡1-3) በጣዖት አምላኪዎች ስትወረርና ስትያዝ (መዝ. 74፡4-8)።
የተተኳሪዎቹን ዐውደ-ጽሑፋዊ ፍሰት ተመልከት (ማለትም፣ የጸሎት ጥያቄዎች)።
1. ማኅበረ-ምዕመናንህን አስብ፣ መዝ. 74፡2
2. መልስ (ማለትም፣ እግሮችህን አንሣ)፣ መዝ. 74፡3
3. አጥፋቸው፣ መዝ. 74፡11
4. ይሄን አስብ፣ መዝ. 74፡18
5. ኪዳንህን ተመልከት፣ መዝ. 74፡20
6. ተነሥ፣ መዝ. 74፡22
7. የራስህን ጉዳይ አድርግ፣ መዝ. 74፡22
8. የሰነፎችን መሳለቅ አስብ፣ መዝ. 74፡22

ለ. የተለያዩትን ሐረጎች ተመልከት፣ የኪዳኑን ሕዝብ የሚገልጹትን።
1. የማሰማርያህ በጎች፣ መዝ. 74፡1
2. የርስትህ ነገዶች፣ መዝ. 74፡2
3. ርግብህን (የምትገዛልህን ነፍስ)፣ 74፡19
4. ችግረኛና ምስኪኑን፣ መዝ. 74፡19፣21

ሐ. መቅደሱን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን የተለያዩ ሐረጎች ተመልከት።
1. የጽዮን ተራራ፣ መዝ. 74፡2
2. ለሁልጊዜ የፈረሱትን፣ መዝ. 74፡3
3. መቅደስህን፣ መዝ. 74፡3፣ 7
4. የመገናኛህን ስፍራ፣ መዝ. 74፡4
5. የስምህን ማደርያ ስፍራ፣ መዝ. 74፡7

መ. አንጓውን ተመልከት (መዝ. 74፡12-17፣ ባብዛኛው የተጠናቀቁ) እግዚአብሔር የፍጥረታት ንጉሥ መሆኑን የሚገልጹ፣ ከዘፍጥረት 1 ምስያዎችን በመጠቀም (መዝሙር 104) እና ዑጋሪቲካዊ ቅኔ።

ሠ. አስገራሚ የሚሆነው የኪዳኑ ሕዝብ ያህዌ ለምን እንደተዋቸው አለማወቃቸው ነው (ማለትም፣በኪዳን ያልታመኑ በመሆናቸው)። እነርሱም ምንም ዓይነት የንስሐ ፍንጭ ሲያቀርቡ አይታዩም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ታማኝነት ያስረግጣሉ፣ ለተስፋዎቹ (እንዴት እንደሚለያይ ተመልከት ከመዝሙር 79 ጋር)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 74፡1-11**

**1አቤቱ፥ ስለ ምን ለዘወትር ጣልኸኝ?**
**በማሰማርያህ በጎች ላይስ ቍጣህን ስለ ምን ተቈጣህ?**
**2አስቀድመህ የፈጠርሃትን ማኅበርህን፥**
**የተቤዠሃትንም የርስትህን በትር፥**
**በእርስዋ ያደርህባትን የጽዮንን ተራራ አስብ።**
**3ጠላት በቅዱሳንህ ላይ እንደ ከፋ መጠን፥**
**ሁልጊዜም በትዕቢታቸው ላይ እጅህን አንሣ።**
**4ጠላቶችህ በበዓል መካከል ተመኩ**
**የማያውቁትንም ምልክት ምልክታቸው አደረጉ።**
**5እንደ ላይኛው መግቢያ ውስጥ**
**በዱር እንጨቶች፥ በመጥረቢያ በሮችዋን ሰበሩ።**
**6እንዲሁ በመጥረቢያና በመዶሻ ሰበሩአት።**
**7መቅደስህን በእሳት አቃጠሉ**
**የስምህንም ማደሪያ በምድር ውስጥ አረከሱ።**
**8አንድ ሆነው በልባቸው በየሕዝባቸው።**
**ኑ፥ የእግዚአብሔርን በዓሎች ከምድር እንሻር አሉ።**
**9ምልክታችንን አናይም**
**ከእንግዲህ ወዲህም ነቢይ የለም**
**እስከ መቼ እንዲኖር የሚያውቅ በኛ ዘንድ የለም።**
**10አቤቱ፥ ጠላት እስከ መቼ ይሳደባል?**
**ስምህን ጠላት ሁልጊዜ ያቃልላልን?**
**11ቀኝህንም በብብትህ መካከል፥**
**እጅህንም ፈጽመህ ለምን ትመልሳለህ?**

**74፡1** የተስፋይቱ ምድር መሸነፍና መወረር (ዘፍ. 1፡1-3) ለመዝሙረኛው አስደንጋጭ ነበር፣ የኪዳን ሕዝቦች ሁሉ የሚያስቡትን ጥያቄ እስኪጠይቅ ድረስ። እነርሱ ራሳቸውን የሚቆጥሩት "ልዩ" አድርገው ነበር (ዘጸ. 19፡5-6፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ተስፋዎች ሁኔታዊ መሆናቸውን ዘንግተዋል፣ በእነርሱ የታማኝነት መታዘዝ ላይ (ዘጸ. 19፡5፤ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)። ከእግዚአብሔር የተትረፈረፈ በረከት እና ጥበቃ የእግዚአብሔር ድርሻ ነበር፣ ነገር ግን የእርሱ ሕዝብ ደግሞ ኃላፊነት አለባቸው (ማለትም፣ ታዛዥነት፣ ዘዳ. 10፡12-13)።

መዝሙረኛው ጸሎቱን ያቀርባል፣ ጥያቄ በመጠየቅ (አአመመቅ)።
1. መዝሙር 74፡1 – ሁለት ጥያቄዎች
2. መዝሙር 74፡10 – አንድ ጥያቄ
3. መዝሙር 74፡11 – አንድ ጥያቄ

▣ **"የቁጣህ ጢስ"** ይህ በጥሬው "የአፍንጫህ ግለት ትንፋሽ" ነው። እሱም ሰዋዊ የሆነ ፈሊጥ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አምላክ እንደ ሰው ሲገለጽ) ለእግዚአብሔር ፍርድ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እሳት)።

**74፡2 “አስብ”** ይህ ከሦስቱ የቃሉ አጠቃቀሞች የመጀመሪያው ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 269፤ ኬቢ. 269፤ *ቃል ተተኳሪ*፤ መዝ. 74፡1፣18፣22)። መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ይጠይቃል፤ ኪዳኑን እንዲያስብ (መዝ. 74፡20፤ “ኪዳንህን አስብ፤” ቢ.ዲ.ቢ. 613፤ ኬቢ. 661፤ *ሂፊል ተተኳሪ*፤ መዝ. 106፡45፤ሌዋ. 26፡42)።

የብኪ. መሪዎች ዘወትር ይሄንን ጸሎት ይጸልያሉ። እነርሱ የሚፈልጉት እግዚአብሔር ተስፋዎቹን እንዲያስብና ኃጢአታቸውን እንዲረሳ ነው! በይዘቱ የሚጸልዩትም ለእግዚአብሔር ምሕረት የተሞላ ባሕርይ ነው፣ ኪዳኑን ማፍረሳቸውን ችላ እንዲል። ይህም የሚያሳየን የሰውን ሥራ ደካማነት ነው፣ መለኮትን እንደመቅረቢያ መንገድ! እሱ ይሆናል፤ ሆኖም፣ ወደ “አዲሱ ኪዳን” በማመልከት (ኤር. 31፡31-34፤ ሕዝ. 36፡22-38)፣ በያህዌ ምሕረት ላይ በመመሥረት፣ እንደ መቀበሉ እና ምስጋናው መሠረት፣ ለመልካም አኗኗር በመጠራት።

▣ **“ተቤዥተሃል”** ይህ የብኪ. ምናባዊ ምስያ ነው፣ የንግድ ቃልን የሚጠቀም (“መግዛት፣” ቢ.ዲ.ቢ. 888፤ ኬቢ. 1111፤ *ቃል የተጠናቀቀ*) የያህዌን ኪዳን ለመግለጽ (ዘጸ. 15፡13፣16፤ ዘዳ. 32፡6)። እነርሱ የእርሱ ናቸው በእርሱ ምርጫ እማ በእርሱ ድርጊት፣ በእነርሱ ሥራ ሳይሆን (ዘዳ. 9፡4-6)።

▣ **“የቀደመው”** ይህ ሐረግ የሚያመለክተው የእግዚአብሔርን ያለፈ ድርጊት ነው። መዝ. 74፡12-17 ላይ እሱ የሚያመለክተው ፍጥረትን ነው፤ እዚህጋ እሱ የሚያመለክተው ዘጸአትን ነው።

በዚህ መዝሙር ላይ የእግዚአብሔር ድርጊቶች በሁለቱም በፍጥረትም ሆነ በዘጸአት ተደባልቀዋል። ለይቶ ለማመልከት አዳጋች ነው፣ የትኛው ፈሊጥ፣ ግሥ፣ ወይም ቁጥር ይሄ እንደሚያመለክት።

ወቅታዊው የኪዳኑ ሕዝቦች ሁኔታ አሳዛኝ ነው (መዝ. 74፡3)። መዝሙረኛው ያለፈውን የእግዚአብሔርን የማዳን/የመታደግ ሥራዎች ይጠቅሳል (ማለትም፣ አንድም የመነሻው ቀውስ (ትርምስ) ወይም የግብፅ እስራት)።

▣ **“የተቤዠሃት”** ግሡ (ቢ.ዲ.ቢ. 145፤ ኬቢ. 169፤ *ቃል የተጠናቀቀ*) ማዕከላዊ ጽንሰ-ሐሳብ ነው (1) ዘጸአት (ዘጸ. 6፡6፤ 15፡13) እና (2) የእስራኤል መሥዋዕታዊ ሥርዓት ሥነ-መለኮታዊ ዓላማ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መዋጀት/መቤዠት።

▣ **“የርስትህም ነገድ”** ይህ ሐረግ ከያዕቆብ አስራ ሦስት ነገዶች አንዱን የሚጠቅስ አይደለም፣ ግን ሁሉንም እንጂ (ኤር. 10፡16፤ 51፡19)። ኢሳ. 63፡17 ላይ “ነገድ” የብዙ ቁጥር ነው፣ ግን ደግሞ የያዕቆብን/እስራኤልን ዘር ያመለክታል፤ እንዲሁም ለአብራም የሆነውን መነሻ ተስፋ (ዘፍጥረት 12፤ 15፤ 17)።

▣ **“የጽዮን ተራራ”** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 2፡6፤ 9፡11፤ እና 20፡2 ላይ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽዮን።

**74፡3** *ሂፊል ተተኳሪ* (“ማንሣት”) ሌላው የጸሎት ጥያቄ ነው፣ እግዚአብሔርን የሚጠይቅ፣ ወደ መቅደሱ ስፍራ እንዲመለስ፣ ወደሚኖርበት (መዝ. 74፡2ሐ፣ “የኖረበት፣” ቢ.ዲ.ቢ. 1014፤ ኬቢ. 1496፤ *ቃል የተጠናቀቀ*)።

ማደሪያው ተወሯል፣ ፈርሷል፣ ብሎም በጣዖት አምላኪ ወራሪዎች ተይዟል (ዝከ. 74፡3-4)።

▣ **“ጠላት”** ጣዖት አምላኪ ወራሪዎች ባሕርያቸው የተገለጸበትን የተለያየ መንገድ ተገንዘብ።

1. ጠላት – መዝ. 74፡3፣10፣18
2. ባላንጣዎች – መዝ. 74፡4፣10፣23
3. ሰነፍ ሰዎች፣ መዝ. 74፡18፣22
4. የዱር አውሬ፣ መዝ. 74፡19

ስለ ታሪካዊ መቼቱ ሁለት ዓይነት ሐሳቦች አሉ፣ ይሄንን ብሔራዊ ሰቆቃ የሚጠሩበት።

1. አዲሱ-ባቢሎናዊ ወረራ በ586 ቅልክ፣ መቅደሱ የተቃጠለበት (መዝሙር 137)
2. የኤዶም ወረራ በ485 ቅልክ፣ መቅደሱ የረከሰበትና የፈረሰበት

**74፡4-8** ግልጽ የሆነውን ትይዩነት ተመልከት፣ “እነርሱ...” የሚለውን በመጠቀም (አአመመቅ)። እነዚህ ቁጥሮች የሚገልጹት ጣዖት አምላኪ ወራሪዎች ያደረጉትን ነው፣ ያህዌ በእስራኤል በኩል ማድረግ የሚኖርበትን የሚያሳዩ።

1. መቅደሱን አፍርሰዋል፣ መዝ. 74፡3ሀ (ሰቆ. 2፡6)
2. ጮኸዋል (ማለትም፣ የድል ተምሳሌት፣ ሰቆ. 2፡7) በመቅደስ፣ መዝ. 74፡4ሀ
3. የጣዖት አምላኪ ምልክታቸውን አስቀምጠዋል (ማለትም፣ ባንዲራዎች፣ ምስሎች፣ መሠዊያ)፣ መዝ. 74፡4ለ
4. የያህዌን ማደሪያ ስፍራ የጥበብ ሥራዎች አፍርሰዋል፣ መዝ. 74፡5-6
5. መቅደሱን በእሳት አቃጥለዋል፣ መዝ. 74፡7ሀ (ማለትም፣ 2 ነገ. 25፡9፤ 2 ዜና. 36፡19)
6. መቅደሱን አርክሰዋል፣ መዝ. 74፡7ለ
7. የእግዚአብሔርን ርስት ሙሉ ለሙሉ ለማፍረስ አስበዋል፣ መዝ. 74፡8ሀ
8. የአካባቢውን የያህዌ ማደሪያዎች ሁሉ አቃጥለዋል፣ መዝ. 74፡8ለ

**74፡4 “ጠላቶችህ”** የተቃጠለው መቅደስ መዝ. 74፡7 ላይ የተጠቀሰው 2 ነገ. 25፡9 ላይ ካለው ጋር ተመሳሳይ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ጠላቶች ባቢሎናውያን ናቸው (ሰቆቃወ ኤርምያስ 2)።

▣ **“በመገናኛህ ስፍራ መካከል ጮኹ”** ይህ ምስያ የሚገልጸው የመቅደሱ ስፍራ በጣዖት አምላኪዎች መያዝ ነው። “መጮኽ” የሚለው ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 980፤ ኬቢ. 1367፤ *ቃል የተጠናቀቀ*) የሚገልጸው የእግዚአብሔር ልዩ የማደሪያ ስፍራ በጭካኔ ድል መሆኑን ነው። ግሡ ጥቅም ላይ የሚውለው ለአንበሶች ነው፣ እሱም የጣዖት አምላኪ ወራሪዎችን በላተኝነትና ኃይል የሚገልጽ (ኢሳ. 5፡29፤ ኤር. 2፡15)።

**74፡5-6** ዳሀድ፣ መልኅቅ መጽሐፍ ቅዱስ ላይ (ቅጽ 17ለ፣ ገጽ 202)፣ ይላል፣ "ቁጥር 5 እና 6 እጅግ ግልጽ ያልሆኑና አስቸጋሪዎች ናቸው፣ ከሞላው መዝሙር መካከል።" ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ የሚገልጸው ጣዖት አምላኪ ወራሪዎች መቅደሱን አንድ ነገር እንዳደረጉት ነው፣ ከማቃጠላቸው በፊት። እሱም የወራሪዎቹን ቍጣ ያሳያል በያህዌ ልዩ የማምለኪያ ስፍራ ላይ። እነርሱ ባጠቃላይ የእስራኤልን አምላክ ለማዋረድ ፈልገዋል።

**74፡5** LXX የመክፈቻ ስንኝ አለው "እንደ ላይኛው መግቢያ ውስጥ" (ማለትም፣ የመቅደሱ የላይኛው መግቢያ)። የዕብራይስጡ ሥር፣ הלע (ቢዲቢ 750-751) ፍችው ሊሆን የሚችለው

1. ጽሑፍ፣ የተጻፈ ቅርስ
2. የሚቃጠል መሥዋዕት ሁሉ
3. መወጣጫ፣ ባለ ደረጃ መውጫ

በዚህ ግሥ እኔ የምገምተው የሚያመለክተው ወደ መቅደስ ወይም ወደ መቅደስ አካባቢ መግቢያ ነው።

**74፡6 "ጠረቢት... በመዶሻም ሰበሩአት"** እነዚህ ሁለት ቃላት (ቢዲቢ 506 እና 476) እዚህጋ ብቻ ነው የሚከሰቱት፣ ብኪ ላይ። ይህ መዝሙር ብዙ ያልተለመዱና ወጣ ያሉ ቃላት አሉት።

የ "መጥረቢያ" እና "ፍላጻ" ምስያ የኤርምያስን የባቢሎን ሠራዊት ገለጻ ሊያንጸባርቅ ይችላል (ኤር. 46፡22-23)።

**74፡8 "ሙሉ ለሙሉ በኃይላችን እንያዛቸው"** ኤምቲ ላይ ርግጠኛ ያለመሆን አለ። ስንኙ የሚያሳየው

1. የኪዳኑ ሕዝብ ፍጹም ጥፋት ነው
2. የመቅደሱና የአካባቢው ማምለኪያ ስፍራዎች መደምሰስ ነው

**74፡9-11** የኪዳኑ ሕዝብ የያህዌን አጠቃላይ መለየትና ዝምታ መገንዘብ አልቻለም። እሱ ምንም አለማድረግን መርጧል፣ ይልቁንም ትንቢት ተናጋሪዎችን ወስዷቸዋል። እነርሱ አንድ ነገር እንዲያደርግ እየለመኑት ነው፣ ስሙን እና መቅደሱን እና ሕዝቡን እንዲያድን!

ችግሩ በርካታ ገጽታዎች አሉት።

1. ወራሪው ባቢሎን ከሆነ፣ እንግዲያውስ ያህዌ በእነርሱ ጎን ይዋጋል።
2. እስራኤል የቁጣው ዕቃ ነው፣ ስለ አመንዝራነታቸውና እምነተ-ቢስነታቸው።
3. ሆኖም፣ ያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ አለው፣ የአብርሃምን ዘር የሚያካትት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።
4. እሱ በእስራኤል ይፈርዳል፣ ይታደጋልም!

**74፡9 "ነቢይ"** ትይዩውን ተመልከት ሰቆ. 2፡9 ላይ።

ልዩ ርዕስ፡ የብኪ ትንቢት

**74፡10** ያህዌ ጣዖት አምላኪዎችን ይጠቀማል፣ በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ፣ ነገር ግን እነርሱንም በመጨረሻ ይፈረድባቸዋል፣ ምክንያቱም

1. እነርሱ ክፉ ስለተናገሩ – ቢዲቢ 357፣ ኬቢ 355፣ ፒል ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 74፡18 (ሌላው ምሳሌ: ሶፎ. 2:8፤10)
2. ስሙን ስለናቁ – ቢዲቢ 610፣ ኬቢ 658፣ ፒል ያልተጠናቀቀ

ያልተጠናቀቀው (ግሥ) የሚገልጸው በሂደት ላይ ያለውን ድርጊት እና አዝማሚያ ነው።

▣ **"እስከ መቼ"** ይህ ተደጋጋሚ ጥያቄ ነው መዝሙር ላይ (መዝ. 6፡3፤ 13፡1፤ 44፡23-24፤ 79፡5፤ 80፡4፤ 85፡5፤ 89፡46፤ 90፡13፤ 94፡3)። ይህ መረጃ ከካህን ወይም ነቢይ የመጣ ነው።

1. መቅደሱ ወድሟል (ካህናት የሉም)
2. ነቢያት የሉም (መዝ. 74፡9)

ይህ መከራ የሚቀበሉ ታማኝ ተከታዮች ሁሉ የሚጠይቁት ጥያቄ ነው፣ በወደቀው፣ ፍጹም ባልሆነው ዓለም። ዓለም ሊወድቅ ይችላል፣ እግዚአብሔር ግን አሁንም ይቆጣጠራል (መዝ. 74፡12-17)።

▣ **"ስምህ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ።

**74፡11** የያህዌ እስራኤልን አለመደገፍ ለዓለም የተሳሳተ መልእክት ያስተላልፋል (ሕዝ. 36፡22-38)። እሱም ማን እንደሆነና ታላቁን ዓላማውን ለዓለም ለማሳየት መሥራት ይኖርበታል (መዝ. 59፡13-15)።

▣ **"ቀኝህ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሲገለጽ (ሰዋዊ)

## መዝሙር ፡ 74፡12-17

**[12]እግዚአብሔር ግን ከዓለም አስቀድሞ ንጉሥ ነው፥**
**በምድርም መካከል መድኃኒትን አደረገ።**
**[13]አንተ ባሕርን በኃይልህ አጸናሃት**
**አንተ የእባቦችን ራስ በውኃ ውስጥ ሰበርህ።**
**[14]አንተም የዘንዶውን ራሶች ቀጠቀጥህ**
**ለኢትዮጵያ ሰዎችም ምግባቸውን ሰጠሃቸው።**

**[15]አንተ ምንጮቹንና ፈሳሾቹን ሰነጠቅህ**
**አንተ ሁልጊዜ የሚፈስሱትን ወንዞች አደረቅህ።**
**[16]ቀኑ የአንተ ነው ሌሊቱም የአንተ ነው**
**አንተ ፀሓዩንና ጨረቃውን አዘጋጀህ።**
**[17]አንተ የምድርን ዳርቻ ሁሉ ሠራህ**
**በጋንም ክረምትንም አንተ አደረግህ።**

**74፥12-17** ይህ አንጓ የመዝሙረኛው የማተኮርያ መንገድ ነበር፣ በእግዚአብሔር አስደናቂ የፈጠራ ሥራዎች (ማለትም፣ ዘፍጥረት 1 ወይም ዘጸአት)። እሱ የፍጥረት አምላክ ነው! እሱ ይሄንን ዓለም ወደ ሕላዌ ያመጣው ለዓላማ ነው። እስራኤል የዚያ ዓላማ ዋነኛ ክፍል ነበር (ማለትም፣ መዝ. 74፥12፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

ትይዩነቱን ተገንዘብ (ማለትም፣ "አንተ..." ቢዲቢ 61፣ ሰባት ጊዜ ከተጠናቀቀ ጊዜ ጋር ጥቅም ላይ ውሏል)፣ እሱም የዘፍጥረት 1 መነሻ ፍጥረትን የሚያመለክት ወይም የግብፅ ሽንፈትና ዘጸአት።

1. ከፋፈልህ (ይህ የዕብራይስጥ ቃል ርግጠኝነት የለውም፣ እሱም ቢዲቢ 830 III ን ይከተላል፣ ነገር ግን ኬቢ 978 ይሄንን አጠቃቀም አያረጋግጥም) ባሕርን
2. የባሕሩን ዘንዶ ራሶች ቀጠቀጥህ (የነጠላ ቁጥር ይሆናል፣ እና ስለዚህ፣ ከሌዋታን ጋር ትይዩ ነው)
3. የሌዋታንን ራሶች ቀጠቀጥህ
4. ምግባቸውን ትሰጣቸዋለህ ለፍጥረትህ/በምድረ-በዳ ለሚኖሩ ሰዎች (ከዐውደ-ጽሑፍ "ፍጥረታት" የተሻለ የሚመስለው፣ ኢሳ. 13፡21-22፤ 23፡13፤ 34፡14፤ ኤር. 50፡39፣ አየተመቅ፣ አእቅ፣ አኢመቅ)
5. የውኃ ምንጮችን ያፈልቃል
6. የሚፈስሱትን ወንዞች ታደርቃለህ
7. ብርሃንን እና ጨለማን ታዘጋጃለህ
8. የምድርን ዳርቻ ሁሉ አጸናህ (ማለትም፣ ባሕር፣ ወቅቶች፣ ሌሊትና ቀን)
9. ወቅቶችን አዘጋጀህ (ማለትም፣ ግብርና)

**74፥12 "ንጉሤ"** ያህዌ እንደ "ንጉሥ" የተገለጸበት ጽንሰ-ሐሳብ እኔ እንደማስበው ሁለት ታሳቢ ማጣቀሻዎች ይኖሩታል።

1. እሱ እውነተኛ መሪ/ሉዓላዊ ነው፣ የኪዳኑ ሕዝብ (መዝ. 89፡1-4፣ መዝ. 44፡4 ላይ ማስታወሻ ተመልከት)
2. ይህ መጠሪያ የተሰጠው በፈጣሪነቱ ባደረገው ሥራና የውኃውን ሁከት ድል በመንሣቱ ነው (ማለትም፣ ራሀብ/ሌዋታን [ከነአናዊ የሁከት አውሬዎች]፣ ኢዮብ 26፡12፤ መዝ. 89፡5-10፤ 93፡1-5፤ ኢሳ. 51፡9)

ብኪ ሁለት ዓይነት የፍጥረት ማሳያዎችን ያቀርባል።

ሀ. ዘፍጥረት 1-2 (ስለ ሕላዌ የሚናገረው)

ለ. መዝሙር 89፤ 96 (ሁከቱን ድል ማድረጉ፣ አፈ-ታሪካዊ ምስያዎችን በመጠቀም፣ ከሱመር፣ ባቢሎን፣ እና ከነአን። ይህ ለእነዚህ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ጣዖታዊ ርዕዮተ ዓለም እውነታዊነት ለመስጠት የታሰበ አይደለም ነገር ግን የያህዌን መልእክት ለእነዚያ ባህል ሕዝቦች ለማዛመድ እንዲረዳ እንጂ፣ ኒዶቲ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 548፣ ቁ. 7 ተመልከት)

**74፥14 "ሌዋታን"** ይህ ቃል በዑጋሪታዊ አፈ-ታሪክ የተለመደ ነው (ኢሳ. 27፥1)። ከታች ያለውን የእኔን ማስታወሻ ተመልከት፣ **ከኢሳ. 27፥1፡**

▣ **"ሌዋታን ፈጣኑ እባብ"** ሌዋታን (ቢዲቢ 531) የዑጋሪታዊ አፈ-ታሪክ የባሕር እንስሳ ይመስላል (ማለትም፣ ኢዮብ 41፥19-21) በኢዮብ 3፡8፤ መዝ. 104፡26፤ አሞጽ 9፡3 ላይ የተጠቀሰ። ሆኖም፣ አንዳንድ ጊዜ እሱ ለክፉ ሕዝብ ተምሳሌት ተደርጎ ይጠቀሳል (መዝ. 74፥13-14፣ ለግብፅ ሊሆን ይችላል)። እሱም ወንዝ በምድራቸው እንደ እባብ እየተምዘገዘገ ሲያልፍ ይመስላል። አንዳንድ ጊዜ ቃሉ በተለይ ከ "ራሃብ" ጋር ይያያዛል፣ እሱም ግብፅን የመጥቀሻ መንገድ (መዝ. 87፡4፤ 89፡9-10፤ እና ኢሳ. 30፡7)። ለእኔ የሚመስለኝ፣ ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ፣ የምንናገረው ስለ ወንዝ ነው፣ ለብሔራዊ ጠላት ተምሳሌት ለሆነ፣ አንድም ግብፅ ወይም ሶርያ (መዝ. 74፡12)። ይህ ቃል በቀላሉ በተምሳሌታዊነት ጥቅም ላይ የሚውልበት ምክንያት ቀደም ሲል በአንዳንድ የከነአናውያን ሥነ-ጽሑፍ አፈ-ታሪክ ጥቅም ላይ በመዋሉ ነው (መዝ. 74፥12-17፤ ጂ. አርከር፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ አዳጋቾች ኢንሳይክሎፔዲያ*፣ ገጽ 239-240)።

ትይዩነት በመካከል አለ

1. በፈጣኑ እባብ (ቢዲቢ 638 I) ወይም የባሕር አውሬ (አአመመቅ የግርጌ ማስታወሻ)
2. ጠማማው የባሕር እባብ
3. በባሕር የሚኖር ዘንዶ

ይኸው ተመሳሳይ ጠቃሽ ይገኛል (1) በዑራቲካዊ ግጥሞች እና (2) ኢሳ. 51፥9፣ "ራሃብ"ን በመጠቀም፣ እሱም ደግሞ "ዘንዶ" በሚለው ቃል የሚገለጽ (ቢዲቢ 1072)።

በዚህ ቁጥር እና በዐውደ-ጽሑፉ መካከል ብቸኛው ግልጽ የሆነ ግንኙነት ኢሳ. 27፥11-12 ነው።

1. ያህዌ እንደ ፈጣሪ፣ መዝ. 74፥11
2. የኤፍራጥስ ፈሳሽ ወንዝ እና የግብፅ ጅረት መዝ. 74፥12
3. የዘመን መጨረሻ ልክ እንደ ዘመን መጀመሪያ ነው (ማለትም፣ ዘፍጥረት 1-2፤ ራዕይ 21-22)

ባጠቃላይ ኢሳይያስ የእነዚህ ጽሑፎች ጥንቅር ነው፣ ለብዙ ዓመታት፣ የተጠናቀረውም በቃላት ወይም በጭብጦች ማቀያየር መሠረት ነው፣ ታሪክ ሳይሆን።

**መዝሙር ፡ 74፥18-21**

> **[18]ይህን ፍጥረትህን አስብ። ጠላት እግዚአብሔርን ተላገደ፥**
> **ሰነፍ ሕዝብም ስሙን አስቈጣ።**
> **[19]የምትገዛልህን ነፍስ ለአራዊት አትስጣት**
> **የችግረኞችህን ነፍስ ለዘወትር አትርሳ።**
> **[20]ወደ ኪዳንህ ተመልከት፥**
> **የምድር የጨለማ ስፍራዎች በኀጥኣን ቤቶች ተሞልተዋልና።**
> **[21]ችግረኛ አፍሮ አይመለስ**
> **ችግረኛና ምስኪን ስምህን ያመሰግናሉ።**

**74፥18-21** ይህ አንጓ የሚያመለክተው የመዝ. 74፥1-11 መነሻ ጸሎት ነው። ያህዌ የማዳንን ሥራ ሊያደርግ ይገባል

1. ጠላት ስሙን ስላጠፋና ስለናቀ (መዝ. 74፥10)
2. እስራኤል የእርሱ ልዩ ሕዝብ ስለሆነ (ዘጸ. 19፥5-6)
3. ለአብርሃም ስለሰጠው ተስፋ (ዘፍ. 12፥1-3)
4. የእርሱ ድርጊቶች ትክክለኛ መልእክት ለአሕዛብ ስለሚያስተላልፉ፣ እሱን እንዲያውቁትና እውቅና እንዲሰጡት ስለሚፈልግ

አራት ተጽኖአዊ እና ሁለት ተተኳሪዎች አሉ።

1. ተተኳሪዎች
   ሀ. አስብ – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 74፥1፥18፥22
   ለ. ተመልከት – ቢዲቢ 613፣ ኬቢ 661፣ ሂፊል ተተኳሪ
2. ተጽዕኗዊ
   ሀ. አሳልፈህ አትስጥ – ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 74፥19
   ለ. አትርሳ – ቢዲቢ 1013፣ ኬቢ 1489፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 74፥19ለ
   ሐ. ችግረኛ አፍሮ አይመለስ – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ ቃል ተጽዕኗዊ ፣መዝ. 74፡21ሀ
   መ. ችግረኛና ምስኪን ስምህን ያመሰግናሉ – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ፒል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ መዝ. 74፡21ለ

**74፥19 "ርግብ (የምትገዛልህን ነፍስ)"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 1076 II) ጥቅም ላይ የዋለው

1. ለመሥዋዕት ለሚቀርብ እንስሳ፣ ዘፍ. 15:9፤ ሌዋ. 1:14፤ 5:7፥11፤ 12:6፥8፤ 14:23፥30፤ 15:14፥29፤ ዘኍ. 6:10
2. ለተንቀሳቃሽ ወፍ፣ ጥ. ሰሎ. 2:12፤ ኤር. 8:7
3. ለኪዳኑ ሕዝብ ተምሳሌት፣ መዝ. 74:19

ሌላ እጅግ የተለመደ ቃል አለ፣ ለ "ርግብ" (ቢዲቢ 401) በላይኛው መንገድ ጥቅም ላይ የሚውል (ማለትም፣ ጥ. ሰሎ. 2:14፤ 5:2፤ 6:9)። መዝሙር 74 ላይ ያለው ቃል ሊጠቅስ የሚችለው

1. ረድኤት አልባነትን
2. ያህዌ በፍርድ ሕዝቡን መሠዋቱን
3. የፍቅር ቃል እሱ ለእስራኤል ያለውን ፍቅር የሚያሳይ (ሆሴ. 7:11፤ 11:11)

የመዝ. 74፥19 ሁለቱም ስንኞች አንድ ዓይነት ነገር ነው የሚጠቅሱት፣ ስለዚህ ቁ. 1 ልክ ሊሆን ይችላል።

አእመቅ፣ LXXን ተከትሎ፣ ማስተካከያ ያቀርባል "ለርግብህ" תורך ፣ "አንተን ለሚያመሰግን፣" תודך። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ. 325 ለአማራጭ ቁ. 1 "ሐ" ደረጃ ይሰጣል፣ (ተገቢ ጥርጣሬ)።

**74፥20** ይህ አስቸጋሪ ቁጥር ነው፣ ለመተርጎም። እሱ ሊያመለክት የሚችለው

1. የወራሪዎችን ዓመጸኝነት
2. የእግዚአብሔር ሕዝብ የግዞት ስፍራ
3. የተሸፈነ የሲኦል ማጣቀሻ፣ የምድር ታችኛ ግዛት (ማለትም፣ እንደ ሲኦል፣ እንዲሁ በመሬት፣ የተስፋይቱ ምድር እንኳ ብትሆን)

እኔ የተሻለ የሚመስለኝ መዝሙር 74፥20 እና 21ን አንድ ላይ መመልከት ነው፣ በኪዳኑ ሕዝብ ላይ የሚሆነው ጭቆና መከራ። ታሪካዊ መቼቱ ባቢሎን ከሆነ፣ ግዞት ነው ማለት ነው፤ ኤዶም ከሆነ፣ እንግዲያውስ በከነአን ምድር ላይ ነው።

**74፡21 "ችግረኛና ምስኪን"** ይህ በተለይ የሚጠቅሰው ለደሀ አይደለም፣ ነገር ግን መከራ ለሚቀበል የኪዳኑ ሕዝብ እንጂ (ማለትም፣ ታማኝ ቅሬታዎች፣ ኒዶቲ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 459)።

**መዝሙር ፡ 74፥22-23**

> **[22]አቤቱ፥ ተነሥ በቀልህንም ተበቀል**
> **ሰነፎች ሁልጊዜም የተላገዱህን አስብ።**
> **[23]የባሪያዎችህን ቃል አትርሳ**
> **የጠላቶችህ ኵራት ሁልጊዜ ወደ አንተ ይወጣል።**

**74፥22-23** ይህ የመጨረሻው ጸሎት ነው፣ ያህዌ እንዲሠራ።

1. ተነሥ – ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ ቃል ተተኳሪ

2. የራስህን ጉዳይ ተመልከት – ቢዲቢ 936፣ ኬቢ 1224፣ *ቃል ተተኳሪ* (*ፊት ለፊት የሆነ የፍርድ መቋቋም፣ የእርሱን ስምና የሕዝቡን ከሚያጎድፉት ጋር፣ መዝ.* 74:3-11)
3. የሰነፎችን መሳለቅ አስብ – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ *ቃል ተተኳሪ*

ያህዌ እባክህን *ሥራ*! አድርግ፣ ዓለም ያውቅ ዘንድ (መዝ. 55:13፤ 83:18፤ ሕዝ. 36:22-38)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ስለ ተስፋይቱ ምድር ወረራና መያዝ ነው። እሱም እግዚአብሔር እንዲያስታውስ ይጠይቃል (መዝ. 74: 2፣18፣22) የኪዳን ተስፋውን፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ለምን እንደፈቀደ ፈጽሞ አይጠቅስም እስራኤል/ይሁዳ እንዲሸነፉ። ለምን እንደዚያ አደረገ?
2. ወራሪዎቹ እነማናቸው?
3. የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ከጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አፈ-ታሪካዊ ምናቦችን ይጠቀማልን? ምን? ለምን?
4. መዝ. 74፡5-6 እና 74፡20 ለመረዳት የሚያስቸግሩት ለምንድነው?
5. “ችግረኛ” የሚለው መዝ. 74፡21 ላይ ማንን ነው የሚጠቅሰው?

# መዝሙር 75
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር ኩራተኛውን ያዋርዳል፣ ጻድቅን ግን ከፍ ያደርጋል<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ፤ የአሳፍ መዝሙር። | ምስጋና ለእግዚአብሔር ጽድቅ ፍርድ | ብሔራዊ ምስጋና ማቅረብ ለእግዚአብሔር ታላቅ ሥራ | እግዚአብሔር ፈራጁ | ሁለንተናዊው ዳኛ |
| 75:1-5 | 75:1 | 75:1 | 75:1 | 75:1 |
| | 75:2-3 | 75:2-5 | 75:2-5 | 75:2-3 |
| | 75:4-5 | | | 75:4-5 |
| 75:6-8 | 75:6-8 | 75:6-9 | 75:6-8 | 75:6-8 |
| 75:9-10 | 75:9 | | 75:9-10 | 75:9-10 |
| | 75:10 | 75:10 | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙረኛው መቼ እንደተናገረ ለማወቅ አስቸጋሪ ነው፣ እንዲሁም ለእግዚአብሔር በሚናገርበት ጊዜ።
1. መዝሙር 75፡1 — መዝሙረኛው መሆኑ ግልጽ ነው
2. መዝሙር 75፡2-3 — አምላክ መሆኑ ግልጽ ነው
3. መዝሙር 75፡4-5 — አንደኛው ሊሆን ይችላል
4. መዝሙር 75፡6-8 — መዝሙረኛው
5. መዝሙር 75፡9 — እግዚአብሔር (ኤምቲ፣ "I")

ለ. እግዚአብሔር ይሠራል እና ከዚያም የእርሱ ድርጊቶች መመዝገብና መብራራት ይኖርባቸዋል (ማለትም፣ ተመስጦ) ለሰው ጸሐፍት፣ የእርሱን መገለጥ ለማስቀመጥ፣ ለቀጣዩ ትውልድ ሊተላለፍ በሚችል መልኩ (ማለትም፣ ቃላዊ፣ በጽሑፍ፣ በታሪኮች)።

ሐ. ፈጣሪ የእያንዳንዱን ሰብዓዊ ፍጡር መጋቢነት ይሻል፣ በሕይወት ስጦታ እና መገለጥ (መዝ. 19፡1-6፣ 7-11)! ፍትሕ አንድ ቀን ይመጣል!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 75፡1-5**

[1]አቤቱ፥ እናመሰግንሃለን እናመሰግንሃለን
ስምህንም እንጠራለን
ተኣምራትህን ሁሉ እናገራለሁ።
[2]ጊዜውን ስቀበል
እኔ በቅን እፈርዳለሁ።
[3]ምድርና በእርስዋ ውስጥ የሚኖሩት ሁሉ ቀለጡ፥
እኔም ምሰሶቿዋን አጠናሁ። ሴላህ
[4]ዓመፀኞችን፡- አትበድሉ አልኋቸው፥
ኃጢአተኞችንም። ቀንዳችሁን አታንሡ
[5]ቀንዳችሁን እስከ ላይ አታንሡ፥
በእግዚአብሔርም ላይ ዓመፅን አትናገሩ።

**75፡1 "እናመሰግናለን"** ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል የተጠናቀቀ*) ሁለቴ ለአጽንዖት ተደግሟል (*መዝ.* 107፡1፣8፣15፣21፣31 *ተመልከት*)። ቃሉ በሂፊል በተደጋጋሚ ጥቅም ላይ ይውላል (65 ጊዜ) መዝሙር ላይ። እሱም ባመዛኙ የሚተረጎመው "ምስጋና" በሚል ነው፣ ግን መዝ. 32፡5 ላይ የሚተረጎመው "መናዘዝ" በሚል ነው።

▣
**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**
**አየተመቅ "ስምህ ቅርብ ነውና"**
**አኢመቅ፣ የተመት፣**
**ፔሺታ፣ LXX "ስምህን እንጠራለን"**
**ጀፒኤስኦኤ "መገኘትህ ቅርብ ነውና"**

ኤምቲ አአመመቅን ይከተላል። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 326) ለሁለተኛው አማራጭ "ሐ" ደረጃ ይሰጣል (ተገቢ የሆነ ጥርጣሬ)፣ ነገር ግን እሱ እጅግ ሁነኛው ዋነኛ ጽሑፍ እንደ ሆነ ይቀበላል።

ችግሩ "ወደ ስምህም በመቅረብ" የሚለው ምን ማለት መሆኑ ነው።

1. ከሕዝብህ ጋር ያንተ መገኘት እንደሆነ እንናገራለን፣ በማዳን ሥራህ
2. አንተ (ማለትም፣ "ስምህ፣" ይኸውም ከያህዌ አካላዊ መገኘት ጋር እኩል የሆነ) አሁን ቅርብ ነህ፣ እናም እንደምትሠራ ተስፋ ማድረግ እንችላለን (ከእስራኤል ኃጢአት የተነሣ ያህዌ ዘወትር አያድናቸውም)
3. ስምህን አንጠራለን ለኪዳን ሕዝብም ያደረግከውን እንናገራለን (ሁለት የተለዩ ድርጊቶች)
4. ኤቢ እሱን ለእግዚአብሔር መጠሪያ አድርጎታል፣ "ቅርቡ" እንዳደረገው
   ሀ. "ልዑሉ" መዝ. 75፡5ሀ ላይ
   ለ. "ድል ነሺው" መዝ. 75፡6 ላይ (ሁለቴ)
   ሐ. "ዘላለማዊው" መዝ. 74፡9 ላይ
   መ. "ጻድቁ" መዝ.74፡10 ላይ
   ኤቢ የሚለው አስራ ሁለት መለኮታዊ ስሞች በዚህ መዝሙር ላይ መኖራቸውን ነው።

▣ **"ሰዎች ተአምራትህን ይናገራሉ"** እስራኤል ለልጆቿ ስለ አባቶቻቸውና ስለ እግዚአብሔር ተስፋ እንደምታስተምር ሁሉ (ዘዳ. 4፡9፣10፤ 6፡7፣20-25፤ 11፡19፤ 32፡46)፣ እነርሱም ተስፋዎችንና አፈጻጸማቸውን ለቀጣዩ ትውልድ ያስተላልፋሉ። እነዚህ "አስደናቂ ድርጊቶች" (ቢዲቢ 810፣ ኬቢ 927፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አስደናቂ ነገሮች) ብርቱ የማዳን፣ የጥበቃ፣ እና የድጋፍ ሥራዎች ናቸው፣ እስራኤል በታሪኳ ሁሉ የተለማመደቻቸው።

ይህ የባሕርይ፣ የተስፋ፣ እና የታመነ የያህዌ ጣልቃ ገብነት መገለጥ፣ መግለጫ ነው

1. እስራኤልን በእምነት ለመጠበቅ
2. አሕዛብን ወደ እምነት ለማምጣት

ኒዶቲ ቅጽ 3 ገጽ 284 የተለያዩ ቃላትን ይዘረዝራል የእግዚአብሔርን ድርጊቶች ለመግለጽ፣ እነርሱም የእርሱን ባሕርይ የሚገልጡ።

1. ተአምራት፣ መዝ. 9፡1፤ 26፡7፤ 40፡5፤ 75፡1
2. ሥራ/ድርጊት፣ መዝ. 44፡1፤ 73፡28፤ 107፡22፤ 118፡17
3. ክብር፣ መዝ. 96፡3
4. ጽድቅ፣ መዝ. 71፡15
5. የታመነ ፍቅር፣ መዝ. 88፡11
6. ታላቅነት፣ መዝ. 145፡6

**75፡2-5 "የተቀጠረውን ሰዓት በመረጥኩኝ ጊዜ"** በእነዚህ ቁጥሮች ላይ ተናጋሪው እግዚአብሔር ነው። እሱ ጊዜውንና ስፍራውን ይወስናል፣ ለዓለም ሁነቶች ሁሉ (ማለትም፣ መዝ. 74፡12-17፤ ዘዳ. 32፡8፤ ሮሜ 9-11)።

1. ወቅቶች – ዘፍ. 1፡14-18፤ መዝ. 72፡17፤ 74፡16-17፤ 104፡19፤ 136፡7-8
2. የአምልኮ ቀናት – ዘፍ. 2፡3፤ ዘጸ. 20፡8-11፤ ሌዋውያን 23፤ ዘኍልቍ 28-29
3. ሁሉም ነገር የሚቀጠረው በእርሱ ነው – መክ. 3፡1-11 (ኢዮብ 14፡5፤ መዝ. 31፡15፤ ሐዋ. 17፡31)

የእግዚአብሔር ሕዝቦች የእርሱን የጊዜ ሰሌዳ አይረዱም። እርሱ በራሱ የጊዜ ሰሌዳ ያድናል፣ በሕዝቡ ሳይሆን። ፍርድ አዘውትሮ፣ ወረራ እንኳ ቢሆን፣ በእርሱ ፍቃድ ነው! ነገር ግን አንድ ቀን ሁሉንም ነገር ቀጥተኛ ያደርጋል!

▣ **"እኔ በቅን እፈርዳለሁ።"** ሁለት ሥነ-መለኮታዊ ነጥቦች አጽንዖት ተሰጥቷቸዋል።

1. እግዚአብሔር በምድር ላይ ይፈርዳል
2. እሱም በፍትሐዊነት ያደርገዋል፣ በእርሱ መገለጥ ላይ በመመሥረት (መዝ. 9:8፤ 58:11፤ 67:4፤ 96:10፣13፤ 98:9)

**75:3 "ምድርና በእርስዋ ውስጥ የሚኖሩት ሁሉ ቀለጡ፥"** ግሣዊው (ቢ.ዲ.ቢ. 556፣ ኬቢ. 555፣ *ኒፋል* አንቀጽ፣ ዘጸ. 15:15፤ ኢያ. 2:9፣24፤ 1 ሳሙ. 14:16፤ ኢሳ. 14:31፤ ኤር. 49:23) የሚያመለክተው የነዋሪውን ሕዝብ ፍርሃት ነው።

የሕዝቡ ልብ ብቻ አልቀለጠም፣ ነገር ግን ምድር ራሷ በፈጣሪዋ/ፈራጇ መገኘት ተጽዕኖ ዐርፎባታል መዝ. 46:6፤ ኢሳ. 24:19-20፤ አሞጽ 9:5፤ ሚኪያስ 1:4፤ ናሆም 1:5)።

አኪ 2 ጴጥ. 3:10 የዚህን ዓለም መጨረሻ ይተነብያል (ማቴ. 5:18፤ 24:35፤ ራዕ. 21:1)።

አዲስ ሰማይና አዲስ ምድር ይመጣሉ። የኤር. 31፡31-34 አዲስ ኪዳን ሙሉ ለሙሉ ተግባራዊ ይደረጋል። መጽሐፍ ቅዱስ ይኼንን አዲስ ዘመን በዔድን ገነት ምናባዊ ምስያ ይገልጸዋል (ዘፍጥረት 1-2ን ከ ራዕይ 21-22 ጋር አስተያይ)።

▣ **"እኔም ምሰሶችዋን አጠናሁ።"** ይህ በጥሬው የምድርን መሠረቶች ማመልከቻ መንገድ ነው (ማለትም፣ የመነሻው ፍጥረት፣ 1 ሳሙ. 2:8፤ ኢዮብ 38:4-6)።

ዮናስ 2፡6 ላይ "የተራሮች መሠረቶች" የፍጥረት ምናባዊ ምስያ ነው። ከታች ያለውን የእኔን ማስታወሻ ተመልከት፣ ከዮናስ 2፡6።

ዮናስ 2፡6 "ወደ ተራሮች መሠረቶች ወረድሁ" ብኪ ሥጋዊ አቅጣጫን ይጠቀማል "ታች" *ሲኦልን* ለመግለጽ (ቢ.ዲ.ቢ. 432፣ ኬቢ 434፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ዘኍ. 16:30፣33፤ መዝ. 55:15፤ ኢሳ. 5:14፤ 14:19)። ሲኦል የሚለው ቃል እና "ጥልቁ" (ቢ.ዲ.ቢ. 1001) ትይዩ ናቸው (መዝ. 30:3)። ይህ የዮናስ ዘይቤአዊ ገለጻ ነው፣ ወደ ምድር ታችኛ ክፍል እንደ ደረሰ የተሰማው፣ ይኸው ልምምዱም ለኢየሱስ አስተያየት መነሻ ሆነ (ማቴ. 12:40-41፤ ሉቃስ 11:30)። ዮናስ እንደሚሞት አምኖ ነበር፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ምሕረትን አደረገለት! የእግዚአብሔር ፍርድ የመጨረሻ ቃሉ አይደለም። በቅጣት ውስጥ ዓላማ አለ።

*መዝሙረኛውና የኪዳኑ ሕዝብ እነዚህ ችግሮች ለምን እንደገጠሟቸው አልተረዱም፣ አምላካቸው ሁሉንም ነገር የሚቆጣጠር መሆኑን አውቀው ሳለ! በሁከት፣ በወረራ፣ እና ፍትሕን በማጣት መካከል እንኳ ቢሆን የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት የጸናና ርግጠኛ ነው (ራዕይ 4-5)! የእርሱ የጊዜ ሰሌዳ የሚነዳው ወደ እርሱ ታላቅ የመዋጀት ዕቅድ ነው፣ በእኛ የአስቸኳይ ፍላጎቶች/ መሻቶች/አስፈላጊ ነገሮች ሳይሆን!*

▣ **"ሴላህ"** መዝሙር 3፡2 ላይ ማስታወሻውንና መግቢያ VII ተመልከት።

**75፡4-5** ፈጣሪ እንደ ሞራል መሪ ይናገራል። የያህዌ ሕግጋት ባሕርዩን ያንጸባርቃሉ። የእርሱ ፍርድ የሚያገኛቸው እነርሱ

1. የሚታበዩ – "አትታበዩ፣" ቢ.ዲ.ቢ. 237፣ ኬቢ. 248፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ኃጢአተኞች – "ቀንዳችሁን ከፍ አታድርጉ፣" ቢ.ዲ.ቢ. 926፣ ኬቢ. 1202 (ሁለቴ)፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. ኩራተኛ – "አትናገሩ. . .፣" ቢ.ዲ.ቢ. 180፣ ኬቢ. 210፣ ፒል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

እሱም የሚመስለው "ኃጢአተኞች" (መዝ. 7:4) በዚህ መዝሙር ላይ

1. ጣዖት አምላኪ ሕዝቦች፣ እነርሱም ወረራ ለማድረግ የሚሞክሩ
2. ትዕቢተኛ እስራኤላውያን (መዝ. 78:3፣8-9፣18-19)

**75:4 "ቀንድ"** ይህ የእንስሳት የኃይል ተምሳሌት እና መለያ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት: በእስራኤል ጥቅም ላይ የሚውሎ ቀንዶች፣ መዝ. 75:10፤ 1 ሳሙ. 2:1፣10፤ ዳንኤል 7-8)።

**75:5**

**አአመመቅ** **"ኩራት"**

**]አኪጀት፣ አየተመቅ፣**

**ፔሺታ** **"አንገት"**

**አእመቅ፣ LXX** **"ዓለት"**

ኤምቲ "አንገት" የሚል አለው (ቢ.ዲ.ቢ. 848)። የተእመቅ "ዓለት" የሚል አለው። ሁለቱ ቃላት እጅግ ተመሳሳይ ናቸው (ማለትም፣ "ዓለት" አንድ ተጨማሪ ተናባቢ አለው)። የተእመቅ የኢዮብ 15፡26ን አጠቃቀም የሚያንጸባርቅ ይመስላል። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 326) ለ "አንገት" "ሐ" ደረጃ ይሰጣል (ተገቢ ጥርጣሬ)። ጀፒኤስኦኤ "የራስ ከበሬታ ትዕቢት" የሚል አለው።

**መዝሙር ፡ 75፡6-8**

**6ከብር ከምሥራቅ ወይም ከምዕራብ**
**ወይም ከምድረ በዳ የለምና**
**7እግዚአብሔር ፈራጅ ነውና**
**ይህን ያዋርዳል ይህንም ያከብራል።**
**8ጽዋ በእግዚአብሔር እጅ ነውና ያልተቀላቀለ የወይን ጠጅ**
**ሞላበት ከዚህ ወደዚያ አገላበጠው፥**
**ነገር ግን አተላው አልፈሰሰም የምድር ኃጢአተኞች ሁሉ ይጠጡታል።**

**75፡6-8** ይህ አንጓ የሚያሳየው የያህዌን ሁለንተናዊ መገኘት ነው፣ ልክ እንደ መዝሙር 139፣ እዚህ ግን ዐውደ-ጽሑፉ የሚያተኩረው እሱ በኃጢአተኞች ላይ የሚያደርገውን ፍርድ ነው (መዝ. 75፡4-5)።

ኃጢአተኞች ዘወትር የበላይነት የያዙ ይመስላል፣ እግዚአብሔር ግን ነገሮችን ቀና ያደርጋል (መዝ. 146፡7፤ 1 ሳሙ. 2፡7፤ ሮሜ 9፤ ያዕቆብ 4፡10)። ይህ መለኮታዊ ድርጊት ተስፋ የሚያደርጉት የተገላቢጦሽ ይሆናል።

**75፡6** ይህ ቁጥር የፍልስጥኤም/ከነአናዊ ምናባዊ ምስያን ተጠቅሟል፣ ሁለንተናዊነትን ለማስረገጥ።

1. ምስራቅ — ምዕራብ
2. የፀሐይ መውጫ — የፀሐይ መግቢያ
3. በረሀ (ደቡብ) — ተራራዎች (ወይም "ከፍታዎች") እነርሱም ሰሜንን የሚያመለክቱ

**75፡8 "ጽዋ"** ይህ ዘወትር የሚያመለክተው የሰውን መዳረሻ ነው፣ እሱም ዘወትር አሉታዊ ነው (ኢሳ. 51፡17፣22፤ ኤር. 25፡15-16፣27-28)። ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 11፡6 ላይ።

▣ **"በደንብ የተደባለቀ"** ይህ የሚያመለክተው የጥንታዊውን የማደባለቅ ዘዴ ነው፣ የተለያዩ ዓይነቶች የኮመጠጡ ፍራፍሬዎችንና የእህል ዓይነቶችን፣ በጣም አስካሪ ከሆኑ መጠጦች። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አልኮል እና አልኮልን አላግባብ መጠቀም።

***መዝሙር ፡ 75፡9-10***

**9እኔ ግን ለዘላለም ደስ ይለኛል፥**
**ለያዕቆብም አምላክ ዝማሬን አቀርባለሁ።**
**10የኀጥኣንን ቀንዶች ሁሉ እሰብራለሁ**
**የጻድቃን ቀንዶች ግን ከፍ ከፍ ይላሉ።**

**75፡9-10** ይህ አንጓ የመዝሙረኛው የመዝጊያ ቃላት ነው።

1. እሱም የያህዌን አስደናቂ ድርጊቶች ይናገራል (መዝ. 75፡1)
2. እሱም ምስጋናን ይዘምራል ለያዕቆብ አምላክ
3. እሱ የያህዌን የጽድቅ ፍርድ የተገላቢጦሽ ያስረግጣል

ይህ የመቅደስ አምልኮ መቼትን ያንጸባርቃል!

**75፡9** ኤምቲ "አውጃለሁ" የሚል አለው፣ LXX እና ፔሺታ ግን፣ "እደሰታለሁ" የሚል አላቸው (አየተመት)። ልዩነቱ አንድ ተናባቢ ነው። LXX ተመሳሳይ ትይዩ ለመመሥረት ይሞክራል፣ በመዝ. 75፡9ሀ እና 9ለ መካከል።

**75፡10 "ይሰብራቸዋል"** ኤምቲ "እኔ አደርጋለሁ" የሚል አለው። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 328) ለዚህ "ሀ" ደረጃ ይሰጠዋል።
ይህ መዝሙር በርካታ ተናጋሪዎች አሉት። መዝ. 75፡9 መዝሙረኛው እንዲሁም 75፡10 ያህዌ ሊሆን ይችላል።

▣ **"ቀንዶች"** ይህ ፈሊጥ በአዎንታዊም ሆነ በአሉታዊ ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል ተገንዘብ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቀንዶች በእስራኤላውያን ጥቅም ላይ የዋሉ)።

1. በአሉታዊ – መዝ. 75፡4-5፣10ሀ፤ ኤር. 48፡25፤ ሰቆ. 2፡17
2. በአዎንታዊ –መዝ. 75፡10ለ፤ 1 ሳሙ. 2፡1፣10፤መዝ. 89፡17፣24፤ 92፡10፤ 112፡9

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በዚህ መዝሙር ላይ ያሉትን የተለያዩ ተናጋሪዎች ዘርዝር።
2. መዝሙሩ እግዚአብሔርን የሚያጎላው እንደ ፈጣሪ ነው ወይስ ፈራጅ?
3. ምናባዊ ምስያዎችን አብራራ
   ሀ. "ምሰሶዎች"
   ለ. "ቀንድ"
   ሐ. "ጽዋ
4. ይህ መዝሙር የሚመለከተው ጊዜያዊውን ፍርድ ነው ወይስ የፍጻሜ ዘመንን ፍርድ?

# መዝሙር 76

## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የያዕቆብ አምላክ የድል ኃይል<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ፤ በበገና። የአሳፍ መዝሙር። | የእግዚአብሔር ግርማ በፍርድ ላይ | የጽዮን ዝማሬ የአምላክን የፍጻሜ ድል በአሕዛብ ላይ ለማክበር | እግዚአብሔር ድል አድራጊው | ውዳሴ ለእግዚአብሔር ለአስደናቂው |
| 76:1-3 | 76:1-3 | 76:1-3 | 76:1-3 | 76:1-3 |
| 76:4-7 | 76:4-6 | 76:4-6 | 76:4-6 | 76:4-6 |
| 76:8-10 | 76:7-9 | 76:7-9 | 76:7-9 | 76:7-9 |
| | | | 76:10 | |
| 76:11-12 | 76:10-12 | 76:10-12 | 76:11-12 | 76:10-12 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ብኪ. የሚጋጭ መገለጥ የሚጠቅስ ይመስላል።
1. የእግዚአብሔር ልዩ ክብካቤና ትኩረት ለአብርሃም ወገኖች (መዝ. 76፡1-7)
2. የእግዚአብሔር መሻት፣ አሕዛብ ሁሉ እርሱን እንዲያውቁት (መዝ. 76፡8-12)

ለ. ይኸው ብርቱ ጉዳይ የአዲስ ኪዳን ዓላማ ነው፣ እሱም በአኪ. የተገለጠ (ማለትም፣ የኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል)። ይሄንን ሥነ-መለኮታዊ ተቃርኖ በሁለት ልዩ ርዕሶች መግለጽ ሞክሬአለሁ።
1. ልዩ ርዕስ፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ
2. ልዩ ርዕስ፡ የብኪ. የመጻዒው ትንበያዎች አልያም የአኪ. ትንበያዎች

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 76፡1-3**
**[1]እግዚአብሔር በይሁዳ ታወቀ፥**
**ስሙም በእስራኤል ታላቅ ነው።**
**[2]ስፍራው በሳሌም፥**
**ማደሪያውም በጽዮን ነው።**
**[3]በዚያም የቀስትን ኃይል፥**
**ጋሻን ሰይፍን ሰልፍንም ሰበረ በዚያም ቀንዶችን ሰበረ።  ሴላህ**

**76፡1-3** ይህ አንጓ የ"ቅዱስ ጦርነትን" ምናባዊ ምስያ ያንጸባርቃል (መዝ. 76፡3)። ታሪካዊ መቼቱ የተከፋፈለው መንግሥት ዘመን ይመስላል (ማለትም፣ 922 ቅ.ል.ክ. 586 ቅ.ል.ክ.) ምክንያቱም ሁለቱንም ይሁዳንና እስራኤልን ስለሚጠቅስ (922-722 ቅ.ል.ክ.)። የትኛው ወታደራዊ ዘመቻ ወይም ወራራ፣ በየትኛው ጣዖት አምላኪ ጎረቤት ወይም የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ኃይል እንደሆነ ርግጠኝነት የለውም።

**76፡1 "*ታወቀ*"** የዕብራይጡ ፍች ሁለት ገጽታዎች አሉት።

1. ስለ አንድ ነገር ወይም ስለ አንድ ሰው መረጃ (ዘፍ. 4፡1፤ ኤር. 1፡5)
2. ግለሰባዊ ግንኙነት

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ።

▣ **"ስሙ"** "ስሙ" *ከኤሎሂም ጋር ትይዩ መሆኑን ተገንዘብ።*
ለ "ስም" ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 1፡6 ላይ። ለ *ኤሎሂም* ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

**76፡2 "ሳሌም...ጽዮን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡

ልዩ ርዕስ፡ ሞሪያ፣ ሳሌም፣ ጄቡስ፣ ኢየሩሳሌም፣ ጽዮን

**76፡3** በርካታ ወታደራዊ ነገሮች ተዘርዝረዋል፣ የያህዌን ወታደራዊ ድል ለማሳየት።

1. ቀስቶች(ቢ.ዲ.ቢ. 905)
2. ጋሻ (ቢ.ዲ.ቢ. 171)
3. ሰይፍ (ቢ.ዲ.ቢ. 352)
4. የጦር መሣርያዎች (ቢ.ዲ.ቢ. 536)

የጠላት የጦር መሣርያዎች ውድመት (መዝ. 46:9፤ ኢሳ. 9:5፤ ሕዝ. 39:9-10) በዛ መንገድ በመታየቱ ምክንያት

1. ጠላት ሙሉ ለሙሉ ተደምስሷል
2. እስራኤል በያህዌ ታምኗል፣ እናም የጦር መሣርያ አላስፈለገውም

▣ **"ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝሙር 3፡2 እና VII መግቢያ ላይ።

## መዝሙር ፡ 76፡4-7

**[4]አንተ በዘላለም ተራሮች ሆነህ**
**በድንቅ ታበራለህ።**
**[5]ልበ ሰነፎች ሁሉ ደነገጡ፥**
**እንቅልፋቸውንም አንቀላፉ**
**ባለጠጎች ሁሉ በእነርሱ እጅ ምንም አላገኙም።**
**[6]የያዕቆብ አምላክ ሆይ፥ ከተግሣጽህ የተነሣ**
**ፈረሰኞች ሁሉ አንቀላፉ።**
**[7]አንተ ግን፥ አንተ ግሩም ነህ**
**ቍጣህን ማን ይቃወማል?**

**76፡4-7** ይህ አንጓ ወታደራዊውን ምስያ ይቀጥላል።

**76:4**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ድንቅ. . .ግርማዊ"** |
| **አኪጀት** | **"ባለክብር እና ግሩም"** |
| **አየተመቅ፣ አእቅ** | **"ባለክብር. . .ግርማዊ"** |
| **አኢመቅ** | **"የሚያብረቀርቅ. . .ስመ-ገናና"** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **"ድንቅ. . .ባለግርማ"** |

እነዚህ ሁለት ቃላትያህዌን ይገልጻሉ።

1. የመጀመሪያው (ቢ.ዲ.ቢ. 21) ሌለኛ ቃል ሊሆን ይችላል "የመብረቅ ብልጭታ" (መዝ. 78:48) የመዝ. 76:3፣ ለሚያበራ ገጽታ አጽንዖት የሚሰጥ (ማለትም፣ ብርሃን) ለያህዌ መገኘት፣ ልክ እንደ ሼክናህ ደመና (የክብር) የዘጸአት።
2. ሁለተኛው (ቢ.ዲ.ቢ. 15) ሊያመለክት የሚችለው የያህዌን ልዕልና ነው፣ በአማልክት ሁሉ ላይ (ጣዖታት)፣ እሱም መዝ. 76:7 (1 ዜና. 16:25፤ መዝ. 89:7፤ 96:4 ላይ የተጠቀሰ)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት፣ ጀፒኤስኦኤ** | **"የአደን ሰለባ ተራራዎች"** |
| **አየተመቅ፣ የተእመቅ፣ LXX** | **"የዘላለም ተራራዎች"** |
| **አኢመቅ** | **"የምርኮ ተራራዎች"** |
| **አእት** | **"ከኮረብታዎች ወረድህ፣ ሰለባህን ወደምትገድልበት"** |

ይህ ሐረግ ለትርጉም አስቸጋሪ እንደሆነ ግልጽ ነው። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 330) ለአየተመት አማራጭ ደረጃ "ሐ" ይሰጠዋል (ተገቢ ጥርጣሬ)። ይህ ምናባዊ ምስያ የዕን. 3፡6 ትኩረት ሊሆን ይችላል። ዩቢኤስ የሚለው የአየተመት ወይም አኢ.መቅ ነው። አእት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያየው እንደ "አንበሳ" ዘይቤ ነው።

**76፡5 "ጽኑአን"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 7 አወቃቀር ቢዲቢ 524) የሚያመለክተው አሻፈረኝ ባይ፣ ጸረ-አምላክ አዝማሚያን ነው (ኢሳ. 46፡12)። ይህም የወራሪዎች ባሕርይ ነው፣ እነርሱም

1. የተገደሉ (ማለትም፣ የተኙ፣ የሞት ዘይቤ)
2. የተዘረፈ (ቢዲቢ 1021፤ ኬቢ 1531፤ *ሂዝፖል* የተጠናቀቀ)

እጅግ ከመፍራታቸው የተነሣ፣ ሊዋጉ አይችሉም (ማለትም፣ በእጃቸው መጠቀም)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"የተዘረፈ"** |
| **አየተመቅ** | **"ምርኳቸው የተወሰደ"** |
| **አእቅ** | **"ያላቸው ሁሉ የተዘረፈ"** |
| **አኢ.መቅ** | **"የተወሰደባቸው" (እንደ ግሥ ጥቅም ላይ የዋለ መዝ. 76፡4ለ)** |
| **LXX** | **"ችግር ላይ የሆኑ"** |
| **የተእመቅ፣ ጀፒኤስኦኤ** | **"ምርኮ የተወሰደባቸው"** |
| **ፔሺታ** | **"በፍርሃት የተመቱ ሆነዋል"** |

ይህ ያልተለመደ መልክ (*ሂዝፖለል*) በኬቢ ተገልጿል (1531) እንደ "መዘረፍ" በሚል። ቢዲቢ (1021) እሱን የሚገልጸው እንደ "የተዘረፈ" ነው። ወራሪዎች የእግዚአብሔርን ከተማ/መቅደስ ለመዝረፍ ፈልገዋል፣ ነገር ግን ራሳቸው ተዘረፉ።

**76፡6 "ከተግሣጽህ የተነሣ"** የያህዌ ብርቱ ድምጽ ድል ይነሣል (መዝ. 80፡16)፣ እሱ እንደፈጠረ (ዘፍጥረት 1፤ ኢዮብ 26:5-11፤ መዝ. 18:7-15፤ 104:5-9)። የእርሱ ድምጽ በዚህ ዓለም ላይ የፍቃዱ ፈሊጥ ነው። እርሱ ይናገራል፣ ተፈጽሟል!

ተግሣጹ ሊሆን የሚችለው (ቢዲቢ 172) የሚጠቅሰው (1) የአንበሳ ጩኸት ከመዝ. 76፡4ለ። ጀፒኤስኦኤ መዝ. 76፡2ን የሚመለከተው የአንበሳን ዋሻ እንደሚጠቅስ ነው (ኢዮብ 38፡39-40 እንደ ማጣቀሻ በመጠቀም) ወይም (2) የውጊያ ጩኸት።

▣ **"የያዕቆብ አምላክ ሆይ"** ይህ መጠሪያ የሚያተኩረው በያህዌ ተስፋዎችና ኪዳን ላይ ነው ከአባቶች ጋር።

▣ **"ሁለቱም ፈረሰኛውና ፈረሱ በብርቱ እንቅልፍ ወደቁ"** ይህ ቃል ከቀይ-ባሕር መከፈል ጋር የተያያዘ ነው፣ እስራኤል እንዲያመልጥ፣ የግብጽን የተመረጡ ወታደራዊ ምድቦች ከደናቸው (ዘጸ. 14:28፣30፤ 15:1፣21)። ይኸው ተመሳሳይ ምስያ በኤርምያስ የባቢሎን ሽንፈት ገለጻ ላይ ይገኛል (ኤር. 51፡21)።

ማለት የሚቻለው መዝ. 76፡6፣ 76፡5ን ዳግም እንደሚያስቀምጠው ነው። እንደዚያ ከሆነ፣ "መተኛት" የተዋጊዎች ጥበባቸውን ማሳየት አለመቻል ነው (ማለትም፣ የእጆች አለመታዘዝ)፣ ሞትን የሚያመለክት ሳይሆን፣ እሱም ዘወትር በ "እንቅልፍ" የሚገለጸውን (ዘዳ. 31:16፤ 2 ሳሙ. 7:12፤ 1 ነገ. 1:21፤ ኢዮብ 7:21)።

ብኪ ዘወትር እግዚአብሔር ሰዎች እንዳይረዱ ሲያደርግ "እንቅልፍ፣" "ማየት፣" "መስማትን" በመጠቀም ነው (ማለትም፣ ዘዳ. 29:4፤ መዝ. 69:23፤ ኢሳ. 6:9-10፤ 29:10፤ ሚኪያስ 3:6)።

**76፡7 "እንዲፈራ"** ይህ ሊያመለክት የሚችለው

1. የኪዳናዊው አምላክና ሕዝቡ ጠላቶች
2. የአሕዛብ ጣዖታት (መዝ. 89:7፤ 96:4፤ 1 ዜና. 16:25)

▣ **"በፊትህ ማን ይቆማል"** ይህ ምናባዊ የፍርድ-ቤት ትዕይንት ነው፣ ዘወትርም ከፍጻሜ ዘመን ጋር የሚያያዝ (ዕዝራ 9:15፤ መዝ. 130:3፤ ናሆ. 1:6፤ ሚል. 3:2፤ ራዕ. 6:17)። የእግዚአብሔር ሕዝብ በዚያን ቀን በፊቱ መቆም ይችላሉ (ማለትም፣ ሉቃስ 21:36፤ ይሁዳ ቁ. 24-25)።

**መዝሙር ፡ 76፡8-10**

**8 ፍርድን ከሰማይ አሰማህ**
**ምድር ፈራች ዝምም አለች፥**
**9 ልበ የዋሃን ያድን ዘንድ**
**እግዚአብሔር ለፍርድ በተነሣ ጊዜ። ሴላህ**
**10 ሰው በፈቃዱ ያመሰግንሃልና፥**
**ከሕሊናቸው ትርፍም በዓልህን ያደርጋሉ።**

**76፡8-10** መዝ. 76፡7 ከዚህ አንጓ ጋር ሊሄድ ይችላል (አኪጀት፣ አየተመቅ፣ አእቅ፣ አኢ.መቅ)።

በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ "የምድር ትሑታን ሁሉ" እነርሱም ያህዌን የሚፈሩና የሚያከብሩትን ነው የሚያመለክተው (መዝ. 40፡13-17)። ሁለንተናዊውን ይዘት ተመልከት፣ እንዲሁም በመካከል ያለውን ተቃርኖ

1. እግዚአብሔር ትሑታንን ያድናል
2. ግን ሁሉም ለእርሱ እውቅና የሚሰጡ (መዝ. 72:11፤ 76:12፤ ፊሊ. 2:6-11)

**76፡10 "ቅሬታ (የተረፉ)"** ይህ ቃል በበርካታ የተለያዩ መልኮች ጥቅም ላይ ውሏል።

ልዩ ርዕስ፡ ቅሬታ (ቢዲቢ 984)፣ በሦስት መልኩ

▣ ይህ አስገራሚ ያህዌን እንደ ተዋጊ ይጠቅሳል (ኢሳ. 59፡17)። ይኸው ተመሳሳይ ምስያ በጳውሎስም ጥቅም ላይ ውሏል፣ ኤፌ. 6፡10-17፣ እሱም "መንፈሳዊ ውጊያን" የሚገልጽ። ያህዌ ድል አድራጊ ነው! ያህዌ በእርሱ ለሚታመኑት አሸናፊያቸው ነው!

ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 669) አአመቅ እና አእመቅ (ደግሞም የተእመቅ) በዚህ ቁጥር ላይ አናባቢዎቹን ይቀይራል፣ ወደ መልከዓ ምድራዊ ስፍራዎች፣ በስተ ሰሜን (ከተማ) እና ወደ ደቡብ (ሕዝብ) የፍልስጥኤም፣ ከመዝ. 76፡11ለ ጋር ትይዩ ለማድረግ።

1. ሰው ( אדם ) ኤዶም ሆኗል (אדם)
2. ቁጣ ( חמה ) ሀማዝ ሆኗል ( חמה)

ችግሩ "ቁጣ" የሚለው ቃል፣ ሁለቴ ጥቅም ላይ መዋሉ ነው፣ መዝ. 76:10 ላይ። የሆን ብሎ የቃላት መቀያየር ካልሆነ በቀር፣ ይህ የአናባቢዎች መቀያየር ግምታዊ ነው፣ ብሎም የማንኛዎቹንም የጥንት ቅጅዎች ድጋፍ አላገኘም።

**መዝሙር ፡ 76፡11-12**

[11]**ለአምላካችን ለእግዚአብሔር ስእለትን ክፈሉ**
**በዙሪያው ያሉ ሁሉ እጅ መንሻን ለሚያስፈራው ያገባሉ።**
[12]**የመኳንንትን ነፍስ ያወጣል**
**በምድርም ነገሥታት ዘንድ ያስፈራል።**

**76፡11-12** መዝ. 76፡7 ከ76፡8 እና 9 ጋር እንደሚሄድ፣ እንዲሁ ደግሞ መዝ. 76፡10 ከ76፡11-12 ጋር ሊሄድ ይችላል (አኪጀት፣ አየተመቅ፣ አእቅ፣ አኢመቅ)። አንቀጹ ጽሑፋዊ ምልክት የለውም። እሱም ተመስጧዊ ገጽታ አይደለም፣ የዕብራይስጡ ጽሑፍ። አንቀጽ ከዐውደ-ጽሑፉ የግድ መረጋገጥ ይኖርበታል (ማለትም፣ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድ ማዕከላዊ እውነት ወይም ርዕሰ-ጉዳይ ይኖረዋል)።

**76፡11ሀ** ይህ የሚገልጸው "ትሑቱን" ነው፣ መዝ. 76፡9 ላይ ያለውን። ሁለት ተተኳሪዎች ጥቅም ላይ ውለዋል፣ ድርጊታቸውን ለመግለጽ።

1. ስእለትን ተሳሉ – ቢዲቢ 623፣ ኬቢ 674፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. *ፈጽሙትም* – ቢዲቢ 1022፣ ኬቢ 1532፣ *ፒል ተተኳሪ* (ሌዋውያን 27፤ ዘኊልቍ 30፤ ዘዳ. 23:21-23)

**76:11ለ** የመዝ. 76:11 ሁለተኛው ስንኝ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ አለው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ("በዙሪያው ያሉ ሁሉ እጅ መንሻን ለእርሱ ያገባሉ…")። ይህ ሦስተኛው ገላጭ ሐረግ ሲሆን፣ የሚጠቅሰውም አንድም

1. የምስጋና መሥዋዕት፣ በስእለቱ ፍጻሜ
2. የሚገባ መሥዋዕት (ሌዋውያን 1-7)

መዝ. 76፡11ሀ የኪዳኑን ሕዝብ ታማኝ ተከታዮች የሚጠቅስ ከሆነ፣ እንግዲያውስ 76፡11ለ የሚያመለክተው በመላው ዓለም ያሉትን ተከታዮችን ነው፣ እነርሱም ያህዌን የሚያመልኩ (መዝ. 45:12፤ 68:29፣31፤ 72:10፤ ኢሳ. 18:7፤ ሶፎ. 3:10)።

**76፡11 "ለእርሱም እጅ-መንሻን ያመጣሉ"** ዘፍ. 49፡10 ላይ የታወቀው የያዕቆብ/እስራኤል ትንቢት ይሁዳን መሲሑ የሚመጣበት ነገድ እንደሆነ ይጠቅሳል። እዚያም *ሺሎህ* הַיֹּשִׁי የሚለው ስም (ቢዲቢ 1010) "ከገዢ፣" ጋር ትይዩ ነው፣ ሆኖም ተናባቢዎቹን መከፋፈል ይቻላል፣ י הַשִׁי፣ "ለእርሱ ስጦታ" ወደሚል፣ አዲስ አናባቢዎችን በመጨመር (ኒዶቲ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 1223)። ይህ ትክክል ከሆነ፣ እንግዲያውስ የያህዌ ከአሕዛብ "እጅ መንሻን" መቀበል ተረጋግጧል (መዝ. 68:29፤ 76፡11፤ ኢሳ. 18:7)። ይህ እጅ-መንሻ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ልዕልናን የማሳያ መንገድ ነው። አንድ ቀን አሕዛብ ወደ ያህዌ ይመጣሉ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

**76፡12** የያህዌ ማዳን/ደኅንነት ሁለንተናዊ እንደሆነ ሁሉ (መዝ. 76፡9)፣ እንዲሁ ደግሞ ፍርዱ ይሆናል (መዝ. 76፡12)።

"መንፈስ" የሚለው ቃል(ሩሕ፣ ቢዲቢ 924) ፍቹው ግለ-ሰብ ነው።

"መቁረጥ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 130፣ ኬቢ 148፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) የዕብራይስጥ ሥር ሲሆን በርካታ ፍችዎች ይኖሩታል።

1. *መቁረጥ* — ማስወገድ
2. *መቁረጥ* — መሰብሰብ፣ እንደ ወይን አዝመራ
3. *መቁረጥ* — የተከበበ ስፍራን በመመሸግ (ማለትም፣ ምሽግ)

ከመዝ. 76፡11 የተነሣ አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ አማራጭ ቁ. 2 የፍጻሜ ዘመን መሰብሰብ እንደሆነ፣ አማኝ ሕዝቦች (ማለትም፣ "መኳንንት፣" ቢዲቢ 617፣ ሕዝ. 28:2) እግዚአብሔርን የሚፈሩ (እሱም አስፈሪ የሆነ፣ ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ *ኒፋል አንቀጽ*) የእርሱን አስፈሪ ኃይል በመጥራት፣ ኢየሩሳሌምንና የኪዳኑን ሕዝቦች በመጠበቅ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝ. 76፥1 የሚያንጸባርቀው የተከፋፈለውን ንጉሣዊ-መንግሥት ጊዜ ነውን?
2. መዝ. 76፥4 ለመተርጎም አዳጋች የሚሆነው ለምንድነው?
3. መዝ. 76፥9 ሌላው ሁለንተናዊ ጠቃሽ ነውን ወይስ በስደት ያሉትን አይሁድ የሚጠቅስ?
4. መዝ. 76፥11-12 ከፊተኞቹ ቁጥሮች ጋር እንዴት ይዛመዳል?

# መዝሙር 77
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ከመከራ መጽናናት የእግዚአብሔርን ብርቱ ድርጊቶች በማስታወስ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ፤ የአሳፍ መዝሙር። | የሚያጽናና የአምላክን የመዋጀት ሥራ ማሰብ | ከግል ችግር ለመታደግ ጸሎት | በችግር ጊዜ መጽናናት | የእስራኤልን ያለፈ ጊዜ ማሰላሰል |
| | | | | 77:1 |
| 77:1-6 | 77:1-3 | 77:1-3 | 77:1-3 | 77:2-3 |
| | | | | 77:4-6 |
| | 77:4-6 | 77:4-10 | 77:4-10 | 77:7-9 |
| 77:7-10 | 77:7-9 | | | 77:10-12 |
| | 77:10-15 | | | |
| 77:11-15 | | 77:11-15 | 77:11-15 | 77:13-15 |
| | | | | 77:16–17 |
| 77:16-20 | 77:16-20 | 77:16-20 | 77:16-20 | 77:18-19 |
| | | | | 77:20 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር ባሕርይ ያደረገው ተጓዳኞችን ነው (8)። መዝሙረኛው እያስታወሰ ነው፣ ባለፉት ጊዜያት እሱ ታደረገውንና ያህዌ ያደረገውን።

ለ. መዝሙር 77:11-15፣ 16-20 በያህዌ ድርጊቶች ላይ ያተኩራል
1. የማዳን
2. የፍጥረት

ሐ. ያህዌ ነው
1. ፈጣሪ
2. ተዋጊ
3. ደጋፊ

መ. መዝሙሩ ለይቶ ይጠቅሳል
1. ያዕቆብን፣ መዝ. 77:15
2. ዮሴፍን፣ መዝ. 77:15

3. ሙሴን፣ መዝ. 77:20
4. አሮንን፣ መዝ. 77:20

የያህዌ ያለፈ ጊዜ የማዳንና የመደገፍ ድርጊቶች ከድሮ ጊዜና ከቀድሞ ጀምሮ ይመስላል። ተለጣጣቂዎቹን ጥያቄዎች ተመልከት መዝ. 77፡7-9።

ሠ. መዝሙር 77፡16-20 ከሥነ-መለኮትና ከምናባዊነት አኳያ ተመሳሳይ ይመስላል፣ በያህዌ ፈጣሪነት መዝ. 74፡13-17 ላይ። የውኃው ምስያ ዘፍጥረት 1ን የሚጠቅስ ይመስላል (ማለትም፣ ፍጥረት) ወይም ዘጸአት 14-15 (ማለትም፣ ዘጸአት)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 77፡1-6**

**[1]በቃሌ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፥**
**ቃሌም ወደ እግዚአብሔር ነው፥ እርሱም አደመጠኝ።**
**[2]በመከራዬ ቀን እግዚአብሔርን ፈለግሁት**
**እጆቼ በሌሊት በፊቱ ናቸው፥ አላረፍሁምም፥**
**ነፍሴም መጽናናትን አልቻለችም።**
**[3]እግዚአብሔርን አሰብሁት ደስ አለኝም**
**ተናገርሁ፥ ነፍሴም ፈዘዘች። ሴላህ።**
**[4]ዓይኖቼ እንዲተጉ ያዝሃቸው**
**ደነገጥሁ አልተናገርሁም።**
**[5]የዱሮውን ዘመን አሰብሁ**
**የዘላለሙን ዓመታት አሰብሁ አጠናጠንሁም**
**[6]በሌሊት ከልቤ ጋር ተጫወትሁ፥**
**ነፍሴንም አነቃቃኋት።**

**77፡1 "በቃሌ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፥"** ይህ ሐረግ ያለ ግሥ ሁለቴ ተደግሟል፣ ለአጽንዖት። መዝሙረኛው ዘወትር አጠንክሮ ይጸልያል፣ ነገር ግን ምንም ሰላም/ውጤት አላገኘም! እሱም በእግዚአብሔር ይታመናል፣ ግን እሱን ይናፍቃል፣ እንዳለፉት ጊዜያት እንዲያደርግ፣ ከኪዳን ሕዝቡ አኳያ።

▣ **"በጣም እጮኻለሁ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 858፣ ኬቢ 1042፣ *ቃል ተጓዳኝ*) ዘጸአት እና የምድረ-በዳ መንከራተት ጊዜ ላይ ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል (ዘጸ. 14:10፣15፤ 17:4፤ ዘኊ. 12:13፤ 20:16፤ ዘዳ. 26:7)። ማለት የሚቻለው የመዝ. 77፡16-19 ገለጻ ይሄንኑ ተመሳሳይ ጊዜ ማመልከቱ ነው። የጸጥታ ጸሎት በጥንታዊው ዓለም አልነበረም። ማንበብ እና መጸለይ ከፍ ባለ ድምፅ ነበሩ!

▣ **"ይሰማኛል"** ይህ ሁለቱም ማስረገጥና መጠየቅ ነው! ቀሪው የዚህ አንጓ ክፍል (መዝ. 77፡1-6) የመዝሙረኛውን ጭንቀት ይገልጻል፣ በያህዌ አጠቃላይ ዝምታ።

**77:2 "በመከራዬ ቀን"** ይህ መዝሙር ላይ ተደጋጋሚ ሐረግ ነው (መዝ. 50:15፤ 86:7፤ በመጠኑ ለየት ያለ የሐረግ አመሠራረት ግን ተመሳሳይ ጽንሰ-ሐሳብ መዝ. 91:15፤ 107:6፣15 ላይ)።

"ቀን" የሚለው አጠቃቀም ጊዜን ይገልጻል እንጂ፣ የተወሰነውን 24 ሰዓት ጊዜ አይደለም። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቀን (ዮም)።

▣ **"እጆቼ በሌሊት ተዘርግተዋል"** "በቀን" የሚለው፣ ስንኝ 1 ላይ ያለው "በሌሊት" ከሚለው ጋር ትይዩ እንደሆነ ተገንዘብ፣ ስንኝ 2 ላይ ካለው። ይህ ቋሚነትን መግለጫ መንገድ ነበር፣ (ማለትም፣ "ያለ መዛል")፤ ያለማቋረጥ የሚደረግ ጸሎት (ማለትም፣ "እጅ መዘርጋት")።

የአይሁድ የጸሎት አቋቋም ዘወትር

1. ተቁሞ
2. እጅ ተነሥቶ
3. ዓይን ተገልጾ፣ ወደ ሰማይ ቀና ብሎ ነበር

ግሡ (ቢዲቢ 620፣ ኬቢ 669፣ *ፒኤል* የተጠናቀቀ) በጥሬው "ማፍሰስ" ነው። ኒዶቲ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 27፣ የሚለው፣ በዚህ ቁጥር ላይ ሁለት ገጽታ ያለው ጸሎት ተደባልቋል (ሰቆ. 2፡19)።

1. በእግዚአብሔር ፊት ልብን በጸሎት ማፍሰስ
2. በእግዚአብሔር ፊት እጆችን ማንሣት/መዘርጋት

▣ **"ነፍሴም መጽናናትን አልቻለችም።"** ያህዌ የማይሰማና የማያደርግ ይመስላል፣ ስለዚህ መዝሙረኛው ጸሎቱን ቀጥሏል! ይህ ከዕንባቆም ጋር ከሥነ-መለኮት አኳያ ትይዩ ነው (ማለትም፣ ዕን. 2፡1)።

**77፡3** ሦስት ተለጣጣቂ *ቃል ተጓዳኞች* አሉ። መዝሙረኛው በጸሎት ሰላም ማግኘት አልቻለም። የያህዌ የፊት ድርጊቶች (መዝ. 77፡5) በኪዳኑ ሕዝቦች አኳያ የሚሠራው የተለወጠ ይመስላል (መዝ. 77፡10ለ)።

▣ **"ሴላህ"** *መዝ.* 3፡2 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት። እሱም በመዝ. 77፡3፣ 9፣ 15 መጨረሻ ላይ መከሰቱን ተገንዘብ። አኢመቅ እና አኪጀት የእሱን አጠቃቀም የሚመለከቱት እንደ ተለያዩ አንጓዎች መዝጊያ ነው።

**77፡4ሀ** ይህ የቅኔ ስንኝ ያደናግራል። መዝሙረኛው ጸሎት ማቆም ይፈልጋል፣ ያህዌ ግን (ቢዲቢ 28፣ ኬቢ 31፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) በጸሎት እንዲቀጥል ያደርገዋል። ይሄንንም መተርጎም ይቻላል፣ እግዚአብሔር ንቁ ሆኖ እንዲቆይ እንዳደረገው፣ በዚህም ምክንያት በጸሎቱ እንዲቀጥል። መዝ. 77፡4-6 የሚያገለግል የሚመስለው ለስድስቱ ጥያቄዎች፣ መዝ. 77፡7-9 ላይ ላሉት እንደ መግቢያ እንዲሆን ነው፣ ከአስፈሪው ታሳቢ ማጠቃለያ ጋር፣ ከመዝ. 77፡10!

የመጀመሪያው አንጓ የሚገልጸው የመዝሙረኛውን ድርጊቶች በዝርዝር ነው (መዝ. 77፡11-12 ላይ እንዳለው)። ይህ የተመዘገበ የመዝሙረኛው ሥነ-መለኮታዊ ትግል ነው፣ ተጨማሪ መረጃ እንዲያገኝ፣ ስለ እግዚአብሔር እና ስለ ፍቃዱ እና ለኪዳኑ ሰዎች ስላለው መንገድ። መዝሙረኛው ግልጽ የሆነውን መቋረጥ ተመልክቷል፣ ባለፈው ጊዜ እና በአሁኑ መካከል ያለውን። ለምን እንደሆነ ሊገነዘብ አልቻለም!

**77፡6 "አስታውሳለሁ... አሰላስላለሁ... በጥልቀት አስባለሁ"** እነዚህ ሦስት ግሦች ናቸው የመዝሙረኛውን የአእምሮ ድርጊቶች የሚገልጹ (መዝ. 143፡5) ከመዛል የተነሣ (መዝ. 77፡1-5) እንዲሁም ከጥርጣሬ (መዝ. 77፡7-10)። እስከ መዝ. 77፡11-15፣16-20 ድረስ ነው ወደ ስሜቱ ተመልሶ የያህዌን ባሕርይና በእስራኤል በኩል ያደረገውን ማመን ያልቻለው።

ሦስት ግሦች (ሁለቱ አንድ ዓይነቶች) መዝ. 77፡11-12 ላይ ድጋሚ መከሰታቸውን ተገንዘብ። እምነት ጊዜና ማሰብን ይወስዳል! የመገለጡ ታማኝነትና የግል ልምምድ ወደ ጸና እምነት ይዋሃዳሉ።

▣ **"በሌሊትም ዝማሬ"** ከመዝ. 42፡8 የተነሣ ይህ ሐረግ የያህዌ አስገራሚ ድርጊቶች ጠቃሽ ሊሆን ይችላል፣ ይኸውም ወደ ሌሊት ጊዜ ምስጋና የሚለውጥ (ሁለቱም፣ ተገንዝበው እና ሳይገነዘቡ)። መዝሙረኛው የቀንና የሌሊት ምስጋናና ሰላምን ያውቃል፣ ነገር ግን አሁን ያለበት ሁኔታ እጅግ የተለየ ነው ።

ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ሦስት ታሳቢዎችን ይሰጣል፣ አአመመቅ "ዝማሬ" ብሎ ለተረጎመው ቃል (ቢዲቢ 618)።

1. ሙዚቃ – נגינתי (MT፣ አአመመቅ)
2. አርምሞ/ማሰላሰል – הגיתי (LXX፣ ፔሺታ፣ አኢመቅ)
3. ኀዘን – נגינותי (አእመቅ)

▣ **"ነፍሴም በጥልቀት ታስባለች"** ግሡ በጥሬው "መፈለግ" ማለት ነው (ቢዲቢ 344፣ ኬቢ 341፣ *ፒል* ያልተጠናቀቀ ከዋው ጋር)። እሱ ወንዴ ነው "መንፈስ" ደግሞ ሴቴ። ስለዚህ፣ እሱ ሊያመለክት የሚችለው

1. መዝሙረኛውን ራሱን
2. እግዚአብሔር እሱን ሲፈልገው (መዝ. 139፡1፣23)

**መዝሙር ፡ 77፡7-10**

**7እግዚአብሔር ለዘላለም ይጥላልን?**
**እንግዲህስ ቸርነቱን አይጨምርምን?**
**8ለዘላለምስ ምሕረቱ ለልጅ ልጅ ተቈረጠችን?**
**የተናገረውስ ቃል አልቆአልን?**
**9እግዚአብሔርስ ሞገሱን ረሳን?**
**በቍጣውስ ምሕረቱን ዘጋውን? ሴላህ።**
**10ይህ ድካሜ ነው አልሁ፥**
**የልዑል ቀኝ እንደ ተለወጠ።**

**77፡7-10** ይህ አንጓ ከመዝሙረኛው የሚረብሽ ጸሎት ጋር ይያያዛል፣ መዝ. 77፡1-6 ላይ ካለው። እሱ መረዳት አልቻለም። እሱም ተለጣጣቂ ጽንፍ የወጡ፣ አስፈሪ ጥያቄዎችን ይጠይቃል፣ ይኸውም የያህዌን የኪዳን ተስፋዎች እና የማይለወጠውን ባሕርዩን የሚጠይቁ ይመስላሉ! እነዚህ እጅግ አስፈሪ ጥያቄዎች ናቸው፣ በብኪ! እሱ ባጠቃላይ አያስብም፣ ችግሩ የተከሰተው ከኃጢአት፣ ከአመንዝራነት (ጣዖት ማምለክ)፣ እና የኪዳኑ ሕዝብ በኪዳኑ ያልታመኑ መሆን ሊሆን እንደሚችል።

የእነዚህ ጥያቄዎች እጅግ አስጨናቂው ገጽታ የሐሰት ድምዳሜው ነው (ማለትም፣ መዝ. 77፡10)! ያህዌ አልተለወጠም (ቢዲቢ 1039፣ ኬቢ 1597) ግን የእርሱ ሕዝብ እንጂ!

ዴሪክ ኪድነር፣ ቲንዳሌ የብኪ ሐተታ (ገጽ 308-309) የሚወስደው አተያይ መዝ. 77፡10 አዎንታዊ የመመለስ ነጥብ ቁጥር ነው፣ መዝ. 77፡11-20ን የሚያስተዋውቅ። "ሴላህ" የሚከሰተው ከመዝ. 77፡9 መጨረሻ ላይ ነው፣ እሱም አንድምታው የሚሆነው መዝ. 77፡10-15 አንጓውን ያደባልቃል (አኪጀት፣ ጀፒኤስኦኤ)። የመዝሙሩ ድምጸት በርግጥ 77፡11-20 ላይ ይቀየራል።

**77፡7-8** መዝሙር 77፡7 እና 8 አራት ቃላት ወይም ሐረጋት አሏቸው፣ እነርሱም የመዝሙረኛውን ስሜት የሚገልጹ፣ ያህዌ በቋሚነት እስራኤልን እንደተወ የተሰማውን።

1. ዘላለም፣ መዝ. 77፡7 – ቢዲቢ 761
2. ዘላለም መዝ. 77፡8 – ቢዲቢ 664
3. ዘላለም መተው ("ፍጻሜው ላይ የሆነ")፣ መዝ. 77፡8 – ቢዲቢ 170፣ ኬቢ 197፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
4. ወደ ፍጻሜው የመጣ፣ መዝ. 77፡8 – ቢዲቢ 189 አወቃቀር ቢዲቢ 189

ለ ቁ. 1 ልዩ ርዕስ ተመልከት: ዘላለም (*ኦላም*)። ይህ ድግግሞሽ የመዝሙረኛውን ፍርሃትና ጥርጣሬ ያሳያል።

**77፡8 "ቸርነት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት: ቸርነት (*ሄሰድ*)።

**77:10 "ልዑሉ"** ይህ የዕብራይስጥ መጠሪያ፣ "ኤሊዮን" (ቢዲቢ 71፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: የመለኮት ስሞች) ከ "ከፍ ያለ" ወይም "የላይኛ" ከሚለው ነው። እሱም ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ የዋለ ነው ዘፍ. 14:18-22፤ ዘኍ. 24:16፤ ዘዳ. 32:8 ላይ፣ እስራኤላውያን ባልሆኑ።

ይህ መዝሙር በርካታ የተለያዩ ስሞችን ለመለኮት ይጠቀማል።

1. ኤሎሂም፣ መዝ. 77:1 ሁለቴ)፣ 3፣ 13፣16
2. አዶናይ፣ መዝ. 77:2፣ 7 ("ጌታዬ")
3. ልዑሉ፣ መዝ. 77:10
4. ያህ፣ መዝ. 77:11 (የያህዌ ምሕጻረ ቃል)
5. ኤል፣ መዝ. 77:9፣ 13፣ 14 (የመለኮት አጠቃላይ ስም፣ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ)

▣

**አአመመቅ፣ አየተመቅ** **"ይህ ኀዘኔ ነው"**
**አኪጀት** **"እሱ ንዴቴ ነው"**
**አኢመቅ** **"ይህ ያቆሰለኝ ነው"**
**ጀፒኤስአኤ** **"እሱ ጥፋቴ ነው"**
**ፔሺታ** **"ይህ አለመጽናቴ ነው"**

አለመግባባት አለ በዘመናዊዎቹ ሊቃውንት መካከል፣ በዕብራይስጡ ሥር አኳያ።

1. ሐለበ፣ ቢዲቢ 317 I – "ማሳመም" (አአመመቅ፣ አየተመቅ፣ አእቅ፣ አእት፣ የተእመቅ፣ ፔሺታ)
2. ሐለበ፣ ቢዲቢ 318 II – "በውዴታ መጠየቅ" (አኢቅ)
3. ኀለበ፣ ቢዲቢ 319 – "መውጋት" (አኢመቅ፣ ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት የሚለው፣ "ቁስለቴ፣" ነው ገጽ 333)

**መዝሙር ፡ 77፡11-15**

**[11]የእግዚአብሔርን ሥራ አስታወስሁ**
**የቀደመውን ተአምራትህን አስታወሳለሁና**
**[12]በምግባርህም ሁሉ እናገራለሁ፥**
**በሥራህም እጫወታለሁ።**
**[13]አቤቱ፥ መንገድህ በመቅደስ ውስጥ ነው**
**እንደ አምላካችን ያለ ታላቅ አምላክ ማን ነው?**
**[14]ተኣምራትን የምታደርግ አምላክ አንተ ነህ።**
**ለሕዝብህ ኃይልን አስታወቅሃቸው።**
**[15]የያዕቆብንና የዮሴፍን ልጆች፥**
**ሕዝብህን በክንድህ አዳንሃቸው።** **ሴላህ።**

**77፡11-15** መዝሙረኛው እንደገና በያህዌ የቀድሞ ድርጊቶች ላይ ማተኮር ይሞክራል (መዝ. 77:11-12፣ 14-15)። እሱም በድጋሚ ያተኩራል፣ በእርሱ የማይለወጥ፣ ልዩ ባሕርይ ላይ (መዝ. 77፡13፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት (አንድ አምላክ ማመን))።

የሆንተቡሎዎቹን ትይዩዎች ተመልከት፣ የቁጥሮቹን፣ መዝ. 77:11-12 ላይ፣ መዝ. 77:6 ላይ ለሆኑት።

**77፡11 "ተአምራት"** እሱም የያህዌን የፍጥረትና የማዳን ሥራ ያመለክታል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አስደናቂ ነገሮች። ተመሳሳይ ቃል (ቢዲቢ 810) መዝ. 77፡14 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እንዲሁም ተመሳሳይ ሥር መዝ. 78:4፣11፣32፤ 107:8፣15፣21፣24፣31፤ 119:18፣27።

**77፡13 "መንገድህ"** "መንገድ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 202) የሚናገረው

1. የእርሱን መገለጥ፣ መዝ. 119:14፤ ኤር. 18:15፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: የእግዚአብሔር መገለጥ ቃላት
2. የእርሱን ባሕርያዊ ድርጊቶች (ማለትም፣ መዝ. 119:3)

▣ **"ቅዱስ"** ይህ የሚያመለክተው

1. የእግዚአብሔርን ባሕርይ
2. የእግዚአብሔርን መቅደስ

ልዩ ርዕስ፡ ቅዱስ

**77፡14-15** ትይዩውን ተመልከት በመዝ. 77፡14ለ እና 15ሀ መካከል ያለውን። ሆኖም፣ በመካከል ልዩነት አለ

1. ብርታትህ በሕዝቦች መካከል (ማለትም፣ እስራኤላዊ ባልሆኑት፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)
2. ክንድህ ሕዝብህን ዋጅታለች (ማለትም፣ እስራኤላውያን)

**77፡15 "የተዋጀ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዋጀ/መዋጀት

**መዝሙር ፡ 77፡16-20**

[16]አቤቱ፥ ውኆች አዩህ፥
ውኆችም አይተውህ ፈሩ ጥልቆች ተነዋወጡ፥
ውኆችም ጮኹ።
[17]ደመኖች ድምፅን ሰጡ፥
ፍላጾችህም ወጡ።
[18]የነጐድጓድህ ድምፅ በዐውሎ ነበረ
መብረቆች ለዓለም አበሩ
ምድር ተናወጠች ተንቀጠቀጠችም።
[19]መንገድህ በባህር ውስጥ ነው፥
ፍለጋህም በብዙ ውኆች ነው፥
አረማመድህም አልታወቀም።
[20]በሙሴና በአሮን እጅ ሕዝብህን
እንደ በጎች መራሃቸው።

**77፡16-20** መዝሙረኛው ወደ ኋላ ተመልሶ ዘፍጥረትን ይመለከታል (መዝ. 77፡15) እንዲሁም ዘጸአትን (መዝ. 77፡20)። የፍጥረት አምላክ የእስራኤል ተዋጊ ሆኗል!

መዝሙሩ የመዝሙረኛውን የመጨረሻ መደምደሚያ አያስቀምጥም። እሱ የያህዌን ማንነት እና ድርጊቶች ማስታወሱና ማሰላሰሉ፣ ድምዳሜውን/ጥያቄውን እንዲተው እንዳደረገው ይታሰባል የመዝ. 77፡10።

**77፡16 "ውኆች"**

ልዩ ርዕስ፡ ውኆች

**77፡20ሀ** ይህ ሐረግ የአሳፍ መዝሙር ባሕርይ ነው (መዝ. 74:1፤ 78:52፣70-76፤ 79:13፤ 80:2)። እንዴት ያለ ርዕስ ነው (ማለትም፣ እረኛ) ለፈጣሪ/ለታዳጊ አምላክ! እሱ ከእኛ ጋር ነው፣ ለእኛም ነው (መዝሙር 23)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር የአንድ ግለሰብ ሰቆቃ (ኀዘን) ነው ወይስ ብሔራዊ ሰቆቃ (ኀዘን)
2. መዝ. 77፡7-10 ከሥነ-መለኮት አኳያ ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድነው?
3. መዝ. 77፡10 አዎንታዊ መልእክት ነው ወይስ አሉታዊ መልእክት?
4. ይህ መዝሙር የተጠቀመው ምናባዊ ምስያ ከፍጥረት ነው ወይስ ከዘጸአት?

# መዝሙር 78
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የአምላክ ምሪት ለሕዝቡ፣ የታመኑ ባይሆኑም<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የአሳፍ ትምህርት | የእግዚአብሔር ቸርነት ለዓመጸኞቹ እስራኤላውያን | የእግዚአብሔር ታላቅ ሥራ ታሪክና የሕዝቡ ያልታመነነት | እግዚአብሔርና ሕዝቡ | የእስራኤል ታሪክ ትምህርት |
| 78:1-4 | 78:1-4 | 78:1-4 | 78:1-4 | 78:1-2 |
| | | | | 78:3-4b |
| | | | | 78:4c-5b |
| 78:5-8 | 78:5-8 | 78:5-8 | 78:5-8 | 78:5c-6b |
| | | | | 78:6c-7 |
| | | | | 78:8 |
| 78:9-16 | 78:9-11 | 78:9-16 | 78:9-16 | 78:9-10 |
| | | | | 78:11–12 |
| | 78:12-16 | | | |
| | | | | 78:13-14 |
| | | | | 78:15-16 |
| 78:17-20 | 78:17-20 | 78:17-20 | 78:17-20 | 78:17-18 |
| | | | | 78:19-20 |
| 78:21-33 | 78:21-25 | 78:21-31 | 78:21-31 | 78:21-22 |
| | | | | 78:23-25 |
| | 78:26-31 | | | 78:26-28 |
| | | | | 78:29-31 |
| | 78:32-33 | 78:32-55 | 78:32-37 | 78:32-33 |
| 78:34-39 | 78:34-39 | | | 78:34-35 |
| | | | | 78:36-37 |
| | | | 78:38-39 | 78:38-39 |
| 78:40-53 | 78:40-55 | | 78:40-51 | 78:40-42 |
| | | | | 78:43-44 |
| | | | | 78:45-46 |
| | | | | 78:47-48 |
| | | | | 78:49-50ሀ |
| | | | | 78:50ለ-51 |
| | | | 78:52-55 | 78:52-53 |
| 78:54-64 | | | | 78:54-55 |
| | 78:56-64 | 78:56-66 | 78:56-64 | 78:56-60 |
| | | | | 78:61-62 |
| | | | | 78:63-64 |
| 78:65-72 | 78:65-66 | | 78:65-69 | 78:65-66 |
| | 78:67-72 | 78:67-72 | | 78:67-69 |
| | | | 78:70-72 | 78:70-72 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የሚያስረግጠው የእምነት ሽግግር ማስፈለጉን ነው፣ ለቀጣዩ ትውልድ (መዝ. 78:1-4፤ 5-8)።
1. የእግዚአብሔርን ድርጊቶች
2. የእግዚአብሔርን መገለጦች

ለ. ይህ መዝሙር የእግዚአብሔርን ታማኝነት ድርጊቶች እና ያልታመነውን እስራኤል ድርጊቶች መዝግቦ ይዟል።
1. ዘጸአት
2. የምድረ-በዳ እንክርት
3. ድል ማድረግ

ሐ. ትይዩዎቹንና ጠቃሾቹን ለመመልከት እጅግ የተሻለው መንገድ የቁጥሮች ሰንጠረዥ ነው፣ ከሌሎች የብኪ ጽሑፎች ጋር በተያያዘ።

መዝ. 78: 12b – ዘኊ. 13:22
መዝ. 78: 13 –ዘጸ. 14:16፣21
መዝ. 78: 14 – ዘጸ. 13:21
መዝ. 78: 15 – ዘጸ. 17:6፤ ዘዳ. 8:15
መዝ. 78: 16 – ዘኊ. 20:8፣10፣11
መዝ. 78: 18 – ዘኊ. 11:4
መዝ. 78: 19 – ዘጸ. 16:3፤ ዘኊ. 11:4፤ 20:3፤ 21:5
መዝ. 78: 20 – ዘኊ. 11:18
መዝ. 78: 21 – ዘኊ. 11:1
መዝ. 78: 22 – ዘዳt. 1:32፤ 9:23
መዝ. 78: 24 – ዘጸ. 16:4
መዝ. 78: 25 – ዘጸ. 16:3
መዝ. 78: 26 –ዘኊ. 11:31
መዝ. 78: 27 – ዘጸ. 16:13
መዝ. 78: 29 – ዘኊ. 11:19፣20
መዝ. 78: 31 – ዘኊ. 11:33፣34
መዝ. 78: 32 – ዘኊ. 14:11፣16-17
መዝ. 78: 33 – ዘኊ. 14:29፣35
መዝ. 78: 34 – ዘኊ. 21:7
መዝ. 78: 35 – ዘኊ. 15:13፤ዘዳ. 9:26፤ 32:4
መዝ. 78: 36 –ዘጸ. 24:7፣8፤ 32:7፣8
መዝ. 78: 38 – ዘጸ.34:6፤ ዘኊ. 14:20
መዝ. 78: 41 – ዘጸ. 14:22
መዝ. 78: 42 – መሳ. 8:24
መዝ. 78: 43 – ዘጸ. 4:21፤ 7:3
መዝ. 78: 45 – ዘጸ. 8:6፣24
መዝ. 78: 46 – ዘጸ. 10:14
መዝ. 78: 47 – ዘጸ. 9:23
መዝ. 78: 48 – ዘጸ. 9:19
መዝ. 78: 49 – ዘጸ. 15:7
መዝ. 78: 50 – ዘጸ. 12:29፣30
መዝ. 78: 52 – ዘጸ. 15:22
መዝ. 78: 53 – ዘጸ. 14:19፣20፣27፣28
መዝ. 78: 54 – ዘጸ. 15:17
መዝ. 78: 58 – ዘጸ. 20:4፤ ሌዋ. 26:1፣30፤ ዘዳ. 4:25፤32:16፣21
መዝ. 78: 59 –ሌዋ. 26:30፤ ዘዳ. 1:34፤ 9:19፤ 32:19
መዝ. 78: 60 – 1 ሳሙ. 4:11
መዝ. 78: 61 – 1 ሳሙ. 4:17
መዝ. 78: 62 – 1 ሳሙ. 4:10
መዝ. 78: 63 – ዘኊ. 11:1፤ 21:28
መዝ. 78: 64 – 1 ሳሙ. 4:17፤ 22:18
መዝ. 78: 66 – 1 ሳሙ. 5:6
መዝ. 78: 69 – 1 ነገሥት 6
መዝ. 78: 70 – 1 ሳሙ. 16:12
መዝ. 78: 71 – 1 ሳሙ. 10:1፤ 2 ሳሙ. 5:2፤ 7:8
መዝ. 78: 72 – 1 ነገ. 9:4

መ. የዚህ እይታ እጅግ የተሻለው ትይዩ፣ ማለትም የእስራኤል ያልታመነ መሆን እና የያህዌ ታማኝነትን የሚያመላክት ነህምያ 9 ነው (ደግሞም ሐዋ. 7)።
1. የአብርሃም መጠራት –መዝ. 78:6-8
2. ዘጸአት – መዝ. 78:9-14
3. የምድረ-በዳ እንክርት – መዝ. 78:15-21
4. ድል ማድረግ – መዝ. 78: 22-25
5. መሳፍንት – መዝ. 78: 26-31

ደግሞም መዝሙር 105-106 ስለ እግዚአብሔር ታማኝነት እና ስለ እስራኤል ታማኝ ያለመሆን እንደሆነ ተመልከት!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 78፡1-4**

[1]ሕዝቤ ሆይ፥ ሕጌን አድምጡ
ጆሮአችሁንም ወደ አፌ ቃል አዘንብሉ።
[2]አፌን በምሳሌ እከፍታለሁ
ከቀድሞ ጀምሮ፥ ያለውንም ተምሳሊት እናገራለሁ።
[3]የሰማነውንና ያውቅነውን፥
አባቶቻችንም የነገሩንን፥
ለሚመጣ ትውልድ ከልጆቻቸው አልሰወሩም።
[4]የእግዚአብሔርን ምስጋናና
ኃይሉን ያደረገውንም ተኣምራት ተናገሩ።

**78፡1-4** መዝሙረኛው የኪዳኑን ሕዝብ ይለምናል፣ ለእግዚአብሔር መገለጥ ሰምቶ ተገቢውን ምላሽ እንዲሰጥ (መዝ. 78፡4ሐ)። እሱም ደግሞ ይለምናቸዋል፣ እውነቱን ለልጆቻቸውና ለልጅ ልጆቻቸው ብሎም ለእያንዳንዱ አዲስ ትውልድ ያስተላልፉ ዘንድ (ዘዳ. 4:9-10፤ 6:7፣20-25፤ 11:19፤ 32:46)።

**78፡1** ሁለት ተተኳሪዎች አሉ።

1. ስሙ (“አድምጡ”) – ቢዲቢ 24፣ ኬቢ 27፣ ሂፊል ተተኳሪ
2. ጆሮአችሁን አዘንብሉ (መልሱ”) – ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ ሂፊል ተተኳሪ

▣ **“ትእዛዝ”** ይህ በጥሬው “ማስተማር” ነው (ቢዲቢ 435)። ይኸም “ከአፌ ቃል” ከሚለው ጋር ትይዩ ነው። በርካታ የተለያዩ የዕብራይስጥ ቃላት አሉ፣ በዚህ መዝሙር ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ለያህዌ መገለጥ።

1. ትእዛዝ/ትምህርት፣ መዝ. 78:1 – ቢዲቢ 435
2. ምስክርነት፣ መዝ. 78:5 – ቢዲቢ 730
3. ሕግ፣ መዝ. 78:5፣10 – ቢዲቢ 435
4. ትእዛዝ፣ መዝ. 78:51 – ቢዲቢ 846
5. ምስክርነቶች፣ መዝ. 78:56 – ቢዲቢ 729 I

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ለእግዚአብሔር መገለጥ ቃላት።

ይህ መዝሙር ለኪዳኑ ሕዝብ ነው የተጻፈው (መዝሙራት አዘውትረው እግዚአብሔርን የሚመለከቱ ናቸው)። ይህ ታሪካዊ ዳሰሳ ጥቅም ላይ የሚውል የሚመስለው (ሚነበበው) በዓመታዊ በዓል ወይም ክብረ-በዓል በመቅደስ ነው፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ ለማበረታታት፣ ካለፈው ተምሮ ለወደፊቱም እንደ እግዚአብሔር ሕዝብ በተገቢው እንዲኖር።

**78:2 “ምሳሌ. . .ተምሳሊት”**

1. ምሳሌ – ቢዲቢ 605
2. ተምሳሊት – ቢዲቢ 295

የግሡ እና ስሙ መልኮች፣ የእነዚህ የሁለቱም ቃላት ሕዝ. 17:2 ላይ ይገኛሉ። ከእኔ ማስታወሻ ላይ ከታች አክያለሁ።

**ሕዝ. 17፡2** ይህ ቁጥር ሁለት ትይዩ ተተኳሪዎች አሉት።

1. “ዕንቆቅልሽ ማቅረብ፣” ቢዲቢ 295፣ ኬቢ 295፣ ቃል ተተኳሪ፣ መሳ. 14:12-19
2. “ምሳሌ መናገር፣” ቢዲቢ 605 II፣ ኬቢ 647፣ ቃል ተተኳሪ፣ ዝከ. 12:23፤ 16:44፤ 17:2፤ 18:2፤ 20:49፤ 24:3

“ዕንቆቅልሽ” የሚለው ቃል (ቢዲቢ 295፣ የግሡን ቢዲቢ 295፣ እና የስሙን፣ ቢዲቢ 295 ዝምድና ተመልከቱ) ማለትም፣ የአንድ መረጃ ፍንጭ የሆነ መግለጫ ወይም ግንዛቤ እንዲያገኝ ተጨማሪ የሆነ (ምሳ. 1:6)።

“ምሳሌ” የሚለው ቃል (ቢዲቢ 605 II፣ የግሡን፣ ቢዲቢ 605 II፣ እና የስሙን፣ ቢዲቢ 605 II ዝምድና ተመልከት) እሱም አጭር የቅኔ መዋቅር ያመጣል፣ ምሳሌ ሊሆን የሚችል፣ እውነትን ለማሳያ መንገድ ንጽጽሮሽን የሚጠቀም።

ሕዝቅኤል እጅግ የላቀ ዘይቤአዊ ቋንቋ ተጠቅሟል፣ ስደተኞቹን ለማሳመን፣ የኢየሩሳሌም ፍርድ ትክክለኛና ርግጠኛ መሆኑን።

ያህዌ እውነትን ለመደበቅ እየሞከረ አይደለም፣ ነገር ግን የመረዳት ቁልፍ የሚመጣው ከእርሱ ተናጋሪዎች/ነቢያት መሆኑን ማስረገጡ እንጂ። የእግዚአብሔር ያለፈው ድርጊት ለእያንዳንዱ ትውልድ ትኩስ ሆኖ መተርጎም ይገባዋል።

ኢየሱስ ይሄንን ቁጥር ጠቅሶታል፣ ማቴ. 13፡35 ላይ። እሱም ይሄንን የተጠቀመበት ሕዝቡ ለምን ትምህርቱን እንዳልተረዱት ለማብራራት ነው። እሱም ደግሞ የእስራኤልን ያለፈ ሁኔታ ዳግም ተርጉሞታል። እርሱ ያስረገጠው የእስራኤል ታሪክ መዳረሻ ታሪክ እርሱ ራሱ መሆኑን ነው! ሆኖም፣ ይህ አስገራሚ ሐቅ፣ ያኔውኑ የራስ ማስረጃ አልነበረም፣ ነገር ግን ሊገለጥ ያለ እንጂ! እርሱ እውነተኛ፣ የመዳረሻው ገላጭ ነው (ማቴ. 5:17-19፣21-48)! እስራኤል በታሪኳ የያህዌን ፍቃድና ዓላማ ለመመልከት እምቢ እንዳለች፣ እንዲሁ ደግሞ የኢየሱስ ትውልድ ከኢሳ. 6:9-10፤ 29:13 ትንቢት ውጭ ኖሮአል። እነርሱ እንደ እስራኤላውያን ነበሩ፣ የመዝ. 78:8!

**78፡4** እያንዳንዱ ትውልድ ስለ እግዚአብሔር ልጆቻቸውን ማስተማር ይኖርባቸዋል። ይህ ተደጋጋሚ አጽንዖት ነው፣ ዘዳግም ላይ። ከእኔ ማስታወሻ **ከዘዳ. 4፡9** እና **6፡7** ላይ አካትቻለሁ።

**4፡9 “ልጆቻቸውን እንዲያስተምሩ”** ይህ ዘዳግም ላይ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (ዘዳ. 4:10፤ 6:7፣ 20-25፤ 11:19፤ 31:13፤ 32:46፤ እና ዘጸ. 10:2፤ 12:26፤ 13:8፣14 ላይ ያለ ማስታወሻ)። አማኞች ልጆቻቸውን ስለ እግዚአብሔር ካላስተማሩ፣ እንደ ወላጅ አልተሳካላቸውም (እንደ መጽሐፍ ቅዱስ አባባል)! እምነት በቤተሰች ውስጥ ይሮጣል (ዘዳ. 5፡10፤ 7፡9)!

**6:7 "እነርሱን በልዩ ትኩረት ልጆችህን ታስተምራለህ"** *ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 1041፣ ኬ.ቢ. 1606፣ *ፒኤል*
የተጠናቀቀ) የሚለው "መሳል" ነው፣ እናም ፒይል ላይ ብቸኛው አጠቃቀም ነው። ቃሉ በዑጋሪታዊ ፍችው "መድገም" ነው። ያም የዚህ ቁጥር መሠረታዊ አጽንዖት ይመስላል። ራቢዎች ይሄንን ቁጥር የሚጠቀሙበት ሼማ ጧትና ማታ "መደገም" እንደሚኖርበት ነው። እኛ ስለ እግዚአብሔር ፍቃድ መናገር ይኖርብናል፣ ለሕይወታችን ስላለው፣ በየቀኑ በምንሠራቸው ሥራዎች ሁሉ አኳያ። የሕይወት ስልት እምነትን ማስተላለፍ የወላጆች ኃላፊነት ነው (ዘዳ. 4፡9፤ 6፡20-25፤ 11፡19፤ 32፡46፣ ሙሉውን ማስታወሻ ተመልከት 4፡9 ላይ)። አስገራሚ የሚሆነው፣ የእነዚህ የማስተማር የተለያዩ ጊዜያት ፍሰቱ የሚያርፈው በአንድ ዓይነት ጽሑፋዊ ፊርጅ መሆኑ ነው፣ እንደ መዝ. 139፡2-6 እና ምሳ. 6፡20-22። ይኸም የወላጆች ኃላፊነት አጽንዖት ምሳ. 22፡6 ላይ ተደግሟል። የእኛ ዘመናዊ ጊዜ የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ቤት የወላጆችን ማሠልጠን ሊተካ አይችልም፣ ነገር ግን በርግጥ ሊደግፈው ይችላል!

▣ ***"ኃይሉን ያደረገውንም ተአምራት"*** ይህ መዝሙር በርካታ ቃላት አሉት፣ የያህዌን የመገለጥና የማዳን ሥራዎች ለመግለጽ።

1. *መዝ.* 78፡4
   *ሀ.* አስገራሚ ሥራዎች ("ምስጋና") – ቢ.ዲ.ቢ. 239፣ ቁ4፣ *መዝ.* 9፡14፤ 35፡28፤ 79፡13፤ 102፡21፤ 106፡2፣47፤ Isa. 43፡21፤ 60፡6፤ 63፡7
   *ለ.* በኃይሉ – ቢ.ዲ.ቢ. 739፣ *መዝ.* 145፡6
   *ሐ.* አስደናቂ ሥራዎች – ቢ.ዲ.ቢ. 810፣ ኬ.ቢ. 927፣ *ኒፋል* አንቀጽ፣ ሚኪያስ 7፡15፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: አስደናቂ ነገሮች (ተአምራት)
2. *መዝ.* 78፡7 – የእግዚአብሔር ሥራዎች – ቢ.ዲ.ቢ. 760፣ *መዝ.* 77፡11፣12፤ ሚኪያስ 2፡7
3. *መዝ.* 78፡11
   *ሀ.* የእርሱ ሥራዎች – ቢ.ዲ.ቢ. 760፣ ከቁ. 2 ጋር ተመሳሳይ፣ እና ከቁጥር 32
   *ለ.* ተአምራቱ – ቢ.ዲ.ቢ. 810፣ ከቁ. 1 ጋር ተመሳሳይ፣ ሐ
4. *መዝ.* 78፡12 – ተአምራቱ – ቢ.ዲ.ቢ. 810፣ ከቁ. 1 ጋር ተመሳሳይ፣ ሐ
5. *መዝ.* 78፡32 – አስደናቂ ሥራዎቹ – ቢ.ዲ.ቢ. 810፣ ከቁ. 1 ጋር ተመሳሳይ፣ ሐ እና *መዝ.* 78፡11
6. *መዝ.* 78፡42 – በኃይሉ ("እጅ") – ቢ.ዲ.ቢ. 388፣ ልዩ ርዕስ: እጅ
7. *መዝ.* 78፡43
   *ሀ.* ምልክቶቹ – ቢ.ዲ.ቢ. 16፣ ቁ. 4፣ ዘጸ. 10፡2፣ *መዝ.* 65፡8
   *ለ.* ድንቆቹ – ቢ.ዲ.ቢ. 68፣ ቁ. 1፣ ዘዳ. 4፡34፤ 6፡22፤ 7፡19፤ 26፡8፤ 29፡2፤ 34፡11፤ ነህ. 9፡10፤ *መዝ.* 105፡27፤ 135፡9፤ ኤር. 32፡20-21
8. *መዝ.* 78፡54 – ቀኙ ረታ – ቢ.ዲ.ቢ. 411፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: እጅ

***መዝሙር ፡ 78፡5-8***

**5 ለልጆቻቸው ያስታውቅ ዘንድ**
**ለአባቶቻችን ያዘዘውን**
**ምስክር በያዕቆብ አቆመ፥**
**በእስራኤልም ሕግን ሠራ**
**6 የሚመጣ፥ ትውልድ የሚወለዱም ልጆች ያውቁ ዘንድ፥**
**ተነሥተው ለልጆቻቸው ይነግራሉ**
**7 ተስፋቸውን በእግዚአብሔር እንዲያደርጉ፥**
**የእግዚአብሔርንም ሥራ እንዳይረሱ፥**
**ትእዛዙንም እንዲጠብቁ**
**8 እንደ አባቶቻቸው እንዳይሆኑ**
**ጠማማና የምታስመርር ትውልድ፥**
**ልብዋን ያላቀናች ትውልድ፥**
**ነፍስዋ በእግዚአብሔር ዘንድ ያልታመነች።**

**78፡5-8** ይህ አንጓ አጽንዖት የሚሰጠው እያንዳንዱ ታማኝ ተከታይ ትውልድ እምነታቸውንና ስለ እግዚአብሔር ፍቃድ ያላቸውን መረዳት ለቤተሰባቸው እንዲያስተላልፉ ነው (ማስታወሻ ተመልከት፣ *መዝ.* 78፡4 ላይ)።

*ታማኝ ተከታዮች ባሕሪያቸው*

1. እምነታቸውን ያኖራሉ ("ተስፋ" ቢ.ዲ.ቢ. 492) በእግዚአብሔር ላይ
2. የእርሱን ሥራዎች አይረሱም ዘዳ. 4፡9፣23፤ 31፡6፡12፤ 8፡11፣14፣19 (ሁለቴ)፤ 9፡7፤ 25፡19
3. ትእዛዛቱን ይጠብቃሉ፣ ዘዳ. 4፡2፣6፣10፤ 5፡1፣10፣29፣32፤ 6፡2፣3፣17፣25፤ 7፡9፣11፣12፤ 27፡1፤ ኢያ. 22፡5

*መዝሙር* 78፡7 አዎንታዊ ጭብጥ ነው፣ የሙሉው መዝሙር፣ እንዲሁም 78፡8 ብርቱ ማስጠንቀቂያ ነው፣ መደረግ ስለሌለበት!

**78፡8** ምንም እንኳ ያህዌ ሁሉንም ነገር ለአብርሃም ዝርያዎች ቢያደርግም፣ እነርሱ ገና እምነተ-ቢስ ነበሩ (ማለትም፣ 2 ዜና. 30፡7፤ ሕዝ. 20፡13፣ 18)። *መዝሙር* 78፡8 እምነተ-ቢሱንና እምነት ያለውን በተቃርኖ ያስተያያል።

1. ጠማማ – ቢ.ዲ.ቢ. 710፣ ኬ.ቢ. 770፣ *ቃል* አንቀጽ፣ ዘዳ. 9፡6፣13፤ 10፡16፤ 31፡27
2. ዓመጸኛ – ቢ.ዲ.ቢ. 598፣ ኬ.ቢ. 632፣ *ቃል* አንቀጽ፣ ዘዳ. 9፡34፤ 31፡27
3. ልባቸውን ያላቀኑ – ቢ.ዲ.ቢ. 465፣ ኬ.ቢ. 464፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ *መዝ.* 78፡37
4. ነፍሳቸው በእግዚአብሔር ዘንድ ያልታመነች – ቢ.ዲ.ቢ. 52፣ ኬ.ቢ. 63፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ

**መዝሙር ፡ 78፡9-16**

[9]የኤፍሬም ልጆች ለሰልፍ ታጥቀው ቀስትንም ገትረው
በሰልፍ ቀን ወደ ኋላ ተመለሱ።
[10]የእግዚአብሔርን ኪዳን አልጠበቁም፥
በሕጉም ለመመላለስ እንቢ አሉ
[11]መልካም ሥራውንና
ያሳያቸውን ተኣምራቱን ረሱ፥
[12]በግብጽ አገርና በጣኔዎስ በረሃ
በአባቶቻቸው ፊት የሠራውን ተኣምራት።
[13]ባሕርን ከፍሎ አሳለፋቸው
ውኆችን እንደ ክምር አቆመ።
[14]ቀን በደመና መራቸው፥
ሌሊቱንም ሁሉ በእሳት ብርሃን።
[15]ዓለቱን በምድረ በዳ ሰነጠቀ
ከጥልቅ እንደሚገኝ ያህል በብዙ አጠጣቸው።
[16]ውኃን ከጭንጫ አወጣ፥
ውኃንም እንደ ወንዞች አፈሰሰ።

**78፡9-16** ይህ አንጓ ዘጸአትን ነው የሚጠቅሰው። አንዳንዶቹ ጠቃሾች ግልጽ አይደሉም (ማለትም፣ መዝ. 78፡9)፣ አንዳንዶቹ ግን (ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት፣ ሐ) እጅግ ግልጽ ናቸው።

ኤፍሬም የሰሜኑን ነገዶች ማመልከቻ መንገድ ሊሆን ይችላል። ዮሴፍ እና ኢያሱ ሁለቱም ከኤፍሬም ነገድ ነበሩ፣ እሱም ከቁጥር አኳያ ትልቁ ነገር የነበረ። ኤፍሬም እና ምናሴ ሁለቱም የዮሴፍ ልጆች ናቸው፣ ከግብፃዊት እናት። ያዕቆብ ኤፍሬምን አስበልጦ ባረከው፣ ከበኵሩ ከምናሴ ይልቅ (ዘፍ. 48፡14-20)።

**78፡10** ግሦቹን ተገንዘብ "መጠበቅ" (ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ *ቃል የተጠናቀቀ፣ አሉታዊ*) እና "መራመድ" (ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246) ትይዩና የኪዳን ሕይወትን የሚገልጹ መሆናቸውን። መታዘዝ በሙሴ ኪዳን ላይ ዓይነተኛ ነው (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)።

**78፡11** የወቅቱ የእስራኤል ትውልድ ያህዌ ለእነርሱ ያደረገውን ሁሉ ረስቶታል፣ በዘጸአት ጊዜ (ዘዳ. 8፡11-20)። ስለዚህ የያህዌን ብርቱ የማዳን ሥራ የሚጠቅሱ ቁጥሮች ብዙ ናቸው።

**78፡12 "ዞአን"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 858) ከግብፅ ሥር "ምሽግ" ነው። ይህ ብርቱ መጠጊያ/ምሽግ ያለው በግብፅ ባሕር ክልል አጠገብ ነው፣ እንዲሁም ደግሞ ጌሴም ይባላል (ምስራቃዊ የዐባይ ወንዝ ዳር)፣ እስራኤላውያን በዮሴፍ ጊዜ የሰፈሩበት። ከተማውም በተለያዩ ስሞች ይታወቃል፣ በተለያዩ ጊዜያት።

1. ዞአን (ዘኍ. 13፡22)
2. ጣኔዎስ
3. አቫሪስ
4. ራምሴስ (ራምሴስ IIን ተከትሎ የተሰየመ፣ ዘጸ. 1፡11፤ 12፡37፤ ዘኍ. 33፡3)

**መዝሙር ፡ 78፡17-20**

[17]ነገር ግን ይበድሉት ዘንድ እንደ ገና ደገሙ፥
ልዑልንም በምድረ በዳ አስቈጡት።
[18]ለነፍሳቸው መብልን ይፈልጉ ዘንድ፥
እግዚአብሔርን በልባቸው ፈተኑት።
[19]እግዚአብሔርን እንዲህ ብለው አሙት።
እግዚአብሔር በምድረ በዳ ማዕድን ያሰናዳ ዘንድ ይችላልን?
[20]ዓለቱን መታ ውኆችም ወጡ፥
ወንዞችም ጐረፉ
እንጀራን መስጠትስ ይችላልን?
ለሕዝቡስ ማዕድን ያዘጋጃልን?

**78፡17-20** ይህ አንጓ የሚቀጥለው ገለጻ፣ ማዕርግ የሌላቸውን፣ የማይታዘዙትን እስራኤላውያንን ነው፣ በዘጸአት እና በምድረ-በዳ የመንከራተት ዘመን።

**78፡18 "እግዚአብሔርን ፈተኑት"** ግሡ (ቢዲቢ 650፣ ኬቢ 702፣ *ፒኤል ያልተጠናቀቀ ከዋው ጋር*) በርካታ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እስሬኤክ እግዚአብሔርን ለመፈተኑ (ዘጸ. 17፡2፤ ዘኍ. 14፡22፤ ዘዳ. 6፡16፤ መዝ. 78፡18፣41፣56፤ 95፡9፤ 106፡14)።

**መዝሙር ፡ 78፡21-33**

[21]እግዚአብሔርም ይህን ሰምቶ ተቈጣ
በያዕቆብም ላይ እሳት ነደደ፥
መዓትም በእስራኤል ላይ መጣ
[22]በእግዚአብሔር አላመኑምና፥
በመድኃኒቱም አልተማመኑምና።
[23]ደመናውንም ከላይ አዘዘ፥
የሰማይንም ደጆች ከፈተ
[24]ይበሉም ዘንድ መናን አዘነበላቸው፥
የሰማይንም እንጀራ ሰጣቸው።
[25]የመላእክትንም እንጀራ ሰው በላ
ስንቅንም እስኪጠግቡ ላከላቸው።
[26]ከሰማይ የምሥራቅን ነፋስ አስነሣ፥
በኃይሉም የደቡብን ነፋስ አመጣ
[27]ሥጋን እንደ አፈር፥
የሚበርሩትንም ወፎች እንደ ባሕር አሸዋ አዘነበላቸው
[28]በሰፈራቸው መካከል፥
በድንኳናቸውም ዙሪያ ወደቀ።
[29]በሉ እጅግም ጠገቡ
ምኞታቸውንም ሰጣቸው።
[30]ከወደዱትም አላሳጣቸውም
መብላቸውም ገና በአፋቸው ሳለ፥
[31]የእግዚአብሔር ቍጣ በላያቸው መጣ፥
ከእነርሱም ከፍ ያሉትን ገደለ፥
የእስራኤልንም ምርጦች አሰናከለ።
[32]ከዚህም ሁሉ ጋር እንደ ገና በደሉ፥
ተአምራቱንም አላመኑም
[33]ቀኖቻቸውም በከንቱ አለቁ፥
ዓመቶቻቸውም በችኰላ።

**78፡21-33** የእስራኤል የማያቋርጥ አለመታዘዝ ያህዌ በእነርሱ ላይ እንዲፈርድ አደረገው። አንድ ምሳሌ የሚሆነን ያህዌ ከተፈጥሮ በላይ የሆነ መብል መስጠቱ ነው (ወፎች)። እሱም በረከቱን እንዴት እንደሚቀበሉ ነገራቸው፣ እነርሱ ግን እንደገና የማይታዘዙ ሆኑ (ዘኁልቍ 11)። ድርጊታቸው ስለ ያህዌ ያላቸውን አዝማሚያ አመላከተ።

1. አላመኑም፣ መዝ. 78፡22
2. አልታመኑም፣ መዝ. 78፡22
3. ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ አሁንም ኃጢአትን ሠሩ፣ መዝ. 78፡32

**78፡22 "ማመን… መታመን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ።

**78፡23 "የሰማይንም ደጆች ከፈተ"** "ሰማያት" (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማያት እና ልዩ ርዕስ፡ ሰማይና ሦስተኛው ሰማይ) የሚታሰቡት በቆዳ እንደተሸፈነ ንፍቀ-ክበብ ነው፣ እንደ ከበሮ። ይህ ንፍቀ-ክበብ ከላይ ያለው ውኃ ወደ ምድር እንዳይወድቅ ይለየዋል። እነሱ የሚያስቡት የሚከፈቱና የሚዘጉ መስኮቶች እንዳሉት ነው፣ በእግዚአብሔር ፍቃድ ላይ ተወስነው፣ እንዲሁም በሰው ልጅ ተግባራት (ዘፍ. 7፡11፤ ሚል. 3፡10)። እግዚአብሔር ይሰጣል

1. ዝናብ (ዘፍጥረት)
2. ምግብ (መዝሙር)
3. ባርኮት (ሚልክያስ)

**78፡24-25 "ከሰማይ ምግብ… የመላእክት እንጀራ"** ይህ የሚጠቅሰው መናን ነው (ዘጸአት 16)። ያህዌ ለጋስ ነው (መዝ. 78፡38)፣ እነርሱ ግን ዓመጸኞች ነበሩ።

መና (ቢዲቢ 577 I) ነጭ ነገር ነው፣ እንደ ጤዛ የሚከሰት። ስያሜውም የመጣው ከዘጸ. 16፡4 ነው "ምንድነው?" የሚል። እሱም ተአምራዊ የምግብ ስጦታ ነው፣ በምድረ-በዳ መንከራተት ጊዜ። እሱም ለአንድ ቀን የሚሆን ብቻ ነው የሚሰበሰበው (የአምላክ የዕለት ስጦታ) አለበለዚያ ይበላሻል (ዘጸ. 16፡16-21)፣ ከሰንበት በፊት ከሆነው ቀን በቀር፣ ለሁለት ቀን የሚበቃ የሚሰበሰብበት፣ እሱም አይበላሽም (ዘጸ. 16፡22-29)። እንደ ዱቄት ይበስላል። እሱም እስራኤላውያን ዮርዳኖስን እንደተሻገሩ ቆመ (ኢያ. 5፡12)።

**78፡27 "አፈር… አሸዋ"** እነዚህ ከሦስቱ ቃላት ሁለቱ ናቸው (አፈር፣ አሸዋ፣ ከዋክብት) ብርካቴ ያለውን ነገር ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉ። እነርሱም በመደበኝነት የሚያያዙት ከአባቶች በርካታ ዝርያዎች ጋር ነው (ማለትም፣ የእግዚአብሔር ተስፋ ለአብርሃም፣ ዘፍ. 12፡2)።

1. አፈር – ዘፍ. 13:16፤ 28:14፤ ዘኁ. 23:10
2. አሸዋ – ዘፍ. 22:17፤ 32:12፤ 2 ሳሙ. 17:11፤ 1 ነገ. 4:20
3. ከዋክብት – ዘፍ. 15:5፤ 22:17፤ 26:4፤ ዘጸ. 32:13፤ ዘዳ. 1:10፤ 10:22፤ 28:62

**78፡29-31** እግዚአብሔር ወፎችን ሰጣቸው፣ ሕዝቡ ግን እንደገና የእግዚአብሔርን ሰጭነት አልታመኑም፣ እናም በርካታ መጠን ያለው አዕዋፍ ሰበሰቡ፣ ለቀጣዩ ጠቀሜታ። ይህም እግዚአብሔርን አላስደሰተውም፣ እናም ፍርዱ በእነርሱ ላይ ወደቀ (ዘኍ. 11፡31-35)።

ደግሞ ደጋግሞ ብኪ ላይ፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ተናግሯል፣ ምን እንደሚያደርጉ፣ እነርሱ ግን አሻፈረኝ አሉ፣ በራሳቸው መንገድም አደረጉት። በየጊዜው ይህ የፍርድ ውጤት ይኖረዋል! ጉዳዩ "መታመን" ነው! እናም አሁንም እሱ ነው!

**78:33**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት** | **"በከንቱ የሚያልቅ"** |
| **አአመመቅ ኅዳግ** | **"ከንቱ፣ እንደ እስትንፋስ"** |
| **አየተመቅ** | **"እንደ እስትንፋስ የሚጠፉ"** |
| **አኢመቅ** | **"በመካከል የሚጠፉ"** |

ይህ ቃል (ቢዲቢ 210 I) መክብብ ላይ ቁልፍ ቃል ነው። ከታች ያለውን የእኔን ማስታወሻ ተመልከት፣ ከመክብብ 1 ላይ።

**መክ. 1፡2 "የከንቱ ከንቱ"** ይህ የዕብራይስጥ የላቀ ማወዳደሪያ ነው (ዝኪ. 1፡2 እና 12፡8)። የቃሉ ፍች "ጤዛ፣" "ትንፋሽ፣" ወይም "ጭጋግ" ነው (ቢዲቢ 210 I፣ ያዕቆብ 4:14)። አጽንዖቱም፣ አንድም (1) ከንቱነት ወይም (2) የሰው ሕይወት ጊዜያዊነት ነው። *ዐውደ-ጽሑፉ* ኋለኛውን ይደግፋል (ኤች. ሲ. ሊዮፖልድ፣ *የመክብብ ማብራሪያ*፣ ገጽ 41)።

ይህ ቁልፍ ቃል እና በዚህ መጽሐፍ ላይ ተደጋጋሚ ሐረግ ነው (መክ. 1፡2፣14፤ 2፡1፣11፣15፣17፣19፣21፣23፣26፤ 3፡19፤ 4፡4፣7፣ 8፣16፤ 5:7፣10፤ 6፡2፣4፣9፣11፣12፤ 7:6፣15፤ 8:10፣14፤ 9:9፤ 11:8፣10፤ 12:8)። ቃሉ ላላ ባለ መልኩ በሌሎችም የጥበብ መጻሕፍት ጥቅም ላይ ውሏል፡ ኢዮብ፣ 5 ጊዜ፤ መዝሙር፣ 9 ጊዜ፤ እና ምሳሌ፣ 3 ጊዜ።

የተለያዩ ንድፈ-ሐሳቦች በዚህ መጽሐፍ ያለውን ጠንከር ያለ መግለጫ እንዴት እንደሚመለከቱት ለመረዳት መግቢያውን ተመልከት፣ ደራሲው፣ ኤች። እኔ አማራጭ ቁ. 1 እመርጣለሁ። ይህ *ሥነ*-መለኮታዊ ቅድመ-ግምት መጽሐፍ የተረጎምኩበት ፈርጅ ይሆናል።

▣ **"ሁሉ ከንቱ ነው"** *ሥሩን* ተገንዘብ፣ "ከንቱ" (ቢዲቢ 210 I)፣ አምስት ጊዜ በዚህ በአንድ ቁጥር ላይ ጥቅም ላይ ውሏል! *የመክብብ የማስታወሻ መጽሐፍ* በዩቢኤስ፣ የሚለው ቃሉን መረዳት የሚኖርብን

1. እንደማይደረስበት
2. *ዕ*ንቆቅልሻዊ
3. ም*ሥ*ጢራዊ
4. ለመረዳት እንደሚያስቸግር ነው

ስለዚህ፣ እሱ ተግባቦት የሚያደርገው እውነታ፣ ሕይወት ምላሽ ባላገኙ ጥያቄዎች እንደተሞላ ነው (ገጽ 4)። የጥበብ እውቀት ያለው ሰው ይሄንን ይረዳል፣ ግን በእግዚአብሔር መታመኑን መቀጠል ይኖርበታል፣ ትእዛዛቱንም መጠበቅ።

ይህ የሚያመለክተው የሕይወትን ርግጠኛ ያለመሆንንና ያልታሰቡ ድርጊቶችን ነው። እነዚህም የወደቀው ሰውነት ውጤት ናቸው፣ ሕይወትን በገዛ ራሳቸው ኃይል ለመኖር ሲሞክሩ፣ ከአምላክ በመለየት። ይህም ውድቀት የተወው ሁኔታ ነው (ዘፍጥረት 3)!

"ሁሉም" የሚለው የዕብራይስጥ ቃል (ቢዲቢ 481)፣ ዘወትር የሚተረጎመው "ሁሉም ነገር፣" በሚል ሲሆን የተለመደ ቃል ነው፣ ነገር ግን አዘውትሮ ጥቅም ላይ የሚውለው መክብብ ላይ ነው (ማለትም፣ 9 ጊዜ ምዕራፍ 1 ላይ፤ 17 ጊዜ ምዕራፍ 2 ላይ፤ 13 ጊዜ ምዕራፍ 3 ላይ፣ ወዘተ)። *ቆሄሊዝ* ይህን አካታች ቋንቋ የሚጠቀመው የእርሱን *ሥነ*-መለኮታዊ አጽንዖት ለመግለጽ ነው

1. ለእግዚአብሔር ተቆጣጣሪነት እና ሉዓላዊነት
2. ለሰው ልጅ ውጤት አልባነትና ጊዜያዊነት

## *መዝሙር* ፡ 78፡34-39

**34በገደላቸውም ጊዜ ወዲያው ፈለጉት**
**ተመለሱ ወደ እግዚአብሔርም ገሠገሡ**
**35ረዳታቸውም እግዚአብሔር፥**
**መድኃኒታቸውም ልዑል አምላክ እንደ ሆነ አሰቡ።**
**36በአፋቸው ብቻ ወደዱት**
**በአንደበታቸውም ዋሹበት**
**37ልባቸው ከእርሱ ጋር አልቀናም፣**
**በቃል ኪዳኑም አልተማመኑትም**
**38እርሱ ግን መሓሪ ነው፥ ኃጢአታቸውንም ይቅር አላቸው፥ አላጠፋቸውምም**
**ቍጣውንም መመለስ አበዛ፥**
**መዓቱንም ሁሉ አላቃጠለም።**
**39ወጥቶ የማይመለስ መንፈስ፥**
***ሥጋ*ም እንደ ሆኑ አሰበ።**

**78፡34-39** ይህ አንጓ የሚገልጸው የሐሰት ንስሐ ነው፣ የተረፉት እስራኤላውያን፣ እንዲሁም ያህዌ በእርሱ ላይ የወሰደው አቋም።

1. የማስመሰል ንስሐ፣ መዝ. 78፡34-35
   ሀ. እነርሱ ተመልክተውታል
   ለ. እነርሱ ወደ እርሱ ተመልሰዋል
   ሐ. እነርሱ እርሱን በደስታ ፈልገውታል

መ. እነርሱ እግዚአብሔር ዓለታቸው/ተቤዢአቸው እንደሆነ አስታውሰዋል
2. የእነርሱ እውነተኛ ሐሳባቸው/ድርጊታቸው (መዝ. 78፡36-37)
ሀ. በሐሰተኝነት ከደውታል (መዝ. 78:36 ሀ እና ለ፣ ኢሳ. 29:13)
ለ. ልባቸው በእርሱ ላይ ጽኑ አልነበረም
ሐ. ለኪዳኑ ታማኞች አልነበሩም
3. የያህዌ አቋም (ርምጃ) (መዝ. 78:38-39)
ሀ. እርሱ ይራራላቸው ነበር (ዘጸ. 34:6፤ ነህ. 9:17፤ መዝ. 103:8፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: የእስራኤል አምላክ ባሕርያት)
ለ. ይቅር አላቸው ( "ሸፈነላቸው፣" ቢዲቢ 497፣ ኬቢ 493፣ ፒሪ IMየተጠናቀቀ)
ሐ. አላጠፋቸውም
መ. ተመለሰ ("መዞር") ከቍጣው
ሠ. ቍጣውን ሁሉ አላነሣባቸውም
ረ. ሥጋ እንደሆኑ አስቧልና (መዝ. 103፡14) ዛሬ እዚህ ሆኖ ነገ የማይኖር
መዝሙር 78፡38-39 በብዙ ራቢያዊ ጽሑፎች ጥቅም ላይ ውሏል። እሱም የእግዚአብሔር ባሕርይ ማጠቃለያ ነው (ዘጸ. 34:6፤ ነህ. 9:17፤ መዝ. 103:8-14)።

**78፡35** የመለኮትን የተለያዩ ስሞች ተመልከቱ።

1. ኤሎሂም (ቢዲቢ 43፣ ኬቢ 52)
2. ዓለታቸው (መዝ. 18:2፤ 19:14)
3. ኤል (ቢዲቢ 42፣ ኬቢ 48)
4. ኤሊዮን (ቢዲቢ 751፣ ኬቢ 832)
5. ተቤዢአቸው (መዝ. 19:14)

**መዝሙር ፡ 78፡40-53**

**40በምድረ በዳ ምን ያህል አስቈጡት፥**
**በበረሃም አሳዘኑት።**
**41ተመለሱ፥ እግዚአብሔርንም ፈተኑት፥**
**የእስራኤልንም ቅዱስ አሳዘኑት።**
**42እነርሱም እጁን አላሰቡም፥**
**ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳነበትን ቀን፥**
**43በግብጽ ያደረገውን ተኣምራቱን፥**
**በጣኔዎስም በረሃ ያደረገውን ድንቁን።**
**44ወንዞቻቸውንም ወደ ደም ለወጠ፥**
**ምንጮቻቸውን ደግሞ እንዳይጠጡ።**
**45ዝንቦችንም በላያቸው ሰደደባቸው፥**
**በሉአቸውም በጓጉንቸርም አጠፋቸው።**
**46ፍሬያቸውን ለኩብኩባ፥**
**ሥራቸውንም ለአንበጣ ሰጠ።**
**47ወይናቸውን በበረዶ፥**
**በለሳቸውንም በአመዳይ አጠፋ።**
**48እንስሶቻቸውን ለበረዶ፥**
**ሀብታቸውንም ለእሳት ሰጠ።**
**49የመዓቱን መቅሠፍት በላያቸው ሰደደ**
**መቅሠፍትን መዓትንም መከራንም**
**በክፉዎች መላእክት ሰደደ።**
**50ለቍጣው መንገድን ጠረገ**
**ነፍሳቸውንም ከሞት አላዳናትም፥**
**እንስሶቻቸውንም በሞት ውስጥ ዘጋ**
**51በኵሮቻቸውን ሁሉ በግብጽ፥**
**የድካማቸውንም መጀመሪያ በካም ድንኳኖች ገደለ።**
**52ሕዝቡን ግን እንደ በጎች አሰማራቸው፥**
**እንደ መንጋም በምድረ በዳ መራቸው።**
**53በተስፋም መራቸው አልፈሩምም፥**
**ጠላቶቻቸውንም ባሕር ደፈናቸው።**

**78፡40-53** በዚህ አንጓ ላይ የመደነጋገር ሁኔታ አለ፣ ያህዌ በእስራኤላውያን በመፍረዱ (መዝ. 78፡40-41) እና በግብፅ ላይ በፈረደበት መካከል፣ በዘጸአት ጊዜ። መቅሠፍቱ መዝ. 78፡43-51 ላይ ተጠቅሷል፣ ዓመጸኞቹን የግብፅ አመራሮች የሚመለከት ነው።

ያህዌ ባልታመኑት እስራኤሎች ላይ በመፍረድ ፈንታ (ማለትም፣ በምድረ-በዳ የመንከራተት ዘመን፣ መዝ. 78፡40-43)፣ እሱ ጋሻቸው ነበር (መዝ. 78:52-53)።

የእስራኤል ያልታመነነት እንዴት እንደተሳለ ተመልከት።

1. ዓምጸውበታል፣ መዝ. 78፥40
2. አጕረምርመውበታል፣ መዝ. 78፥40
3. ፈትነውታል፣ መዝ. 78፥41
4. ቅር አሰኙተውታል፣ መዝ. 78፥41
5. የእርሱን ኃይል/ምልክቶች/ተአምራቱን አላሰቡም፣ መዝ. 78፥42

**78፥44-51** እነዚህ ቁጥሮች የሚገልጹት የግብፅን መቅሠፍት ነው።
1. ውኃ/ወንዝ ወደ ደም – ዘጸ. 7:17-19
2. ዝንቦች – ዘጸ. 8:16-18
3. እንቁራሪቶች – ዘጸ. 8:2-6
4. ፌንጣ/አንበጣ – ዘፍ. 8:21፤ 10:4-6
5. በረዶ –ዘጸ. 9:18
6. መቅሠፍት/ቸነፈር – ዘጸ. 9:8-10
7. የበኵሮች ሞት – ዘጸአት 11

ቅደም ተከተላቸውና ቁጥራቸው ልክ አይደለም፣ ነገር ግን በግልጽ አስሩ የዘጸአት 7-11 መቅሠፍት የተጠቀሱት ናቸው፣ የያህዌ ፍርድ ፈሊጦች ከመሆናቸው በቀር።

**78፥49** ይህ ቁጥር ተለጣጣቂ የጸሎት ቃላትን ይጠቀማል፣ የእግዚአብሔርን ቍጣ ለመግለጽ (መዝ. 78፥38)።
1. የሚነድ ቁጣ – ቢዲቢ 354 አወቃቀር ቢዲቢ 60 I
2. ቁጣ – ቢዲቢ 720
3. ብስጭት – ቢዲቢ 276
4. ችግር – ቢዲቢ 865
5. የአጥፊ መላእክት ጭፍራ

ቁጥር 5 ፈሊጥ ነው እሱም የእግዚአብሔርን የቁጣ ዕቃዎች ሰውኛ የሚያደርግ። በዘጸአት የተመለከተው የበኵሮች ሞት፣ ምልክት ባልተደረገባቸው ቤቶች፣ እግዚአብሔር ራሱ ነው ሁነቱ እንዲሆን ያደረገው (ዘጸ. 11:4፤ 12:12)። ይህም ኋላ ላይ የይሁዲነት መረዳት ሆነ "የሞት መልአክ" በሚል (ማለትም፣ ሳማኤል ወይም አዝራኤል")፣ መጽሐፍ ቅዱስ ግን እሱን ለይቶ አይጠቅሰውም፣ ምንም እንኳ 2 ሳሙ. 24:16፤ 2 ነገ. 19:35፤ 1 ዜና. 21:15፤ኢሳ. 37:36፣ አንዱን ቢያመለክቱም። ራቢዎች ደግሞ የሚያስረግጡት መዝ. 89፥48 የሚያመለክተው እሱን እንደሆነ ነው (ማለትም፣ ታርጉም፣ "የሞትን መልአክ መመልከት") ሥነ-መለኮታዊ ነጥብ የሚሆነው እግዚአብሔር ነው፣ ሰይጣን ወይም መልአክ ሳይሆን፣ ሞትን የሚቆጣጠረው!

**78፥50** ይህ የድርጊት ዝግጅት ፈሊጥ ነው። ቀጣዮቹ ሁለቱ መስመሮች የሚያሳዩት በዚህ ጉዳይ ላይ የያህዌ ፍርድ ነው።

**78፥52** እግዚአብሔር እንደ እረኛ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ በአሳፍ መዝሙር። ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 77፥20 ላይ።

**78፥53** ይህ ቁጥር ሁለት ታሪካዊ ጠቃሾች አሉት።
1. "መራቸው" የሚያመለክተው ሼክናህን ነው የክብር ደመና፣ እሱም እስራኤላውያንን የመራ (ዘጸ. 13:21፤ 14:19፣24፤ 33:9፣10)
2. "ጠላቶቻቸውንም ባሕር ደፈናቸው" የሚያመለክተው የኤርትራን ባሕር መከፈልና ከዚያም የተመለሰው ውኃ የግብፅን የተመረጡ ወታደሮች እና ሠረገሎች ማስጠሙን ነው (ዘጸአት 14-15)

## መዝሙር ፡ 78፥54-64

**54 ወደ መቅደሱም ተራራ አገባቸው፥**
**ቀኙ ወደ ፈጠረችው ወደዚህች ተራራ**
**55 ከፊታቸውም አሕዛብን አባረረ፥**
**ርስቱንም በገመድ አካፈላቸው፥**
**የእስራኤልንም ወገኖች በቤታቸው አኖረ።**
**56 ነገር ግን ልዑል እግዚአብሔርን ፈተኑት አስቈጡትም፥**
**ምስክሩንም አልጠበቁም**
**57 ተመለሱም እንደ አባቶቻቸውም ከዱ**
**እንደ ጠማማ ቀስትም ተገለበጡ**
**58 በኮረብታ መስገጃዎቻቸውም አስቈጡት፥**
**በተቀረጹ ምስሎቻቸውም አስቀኑት።**
**59 እግዚአብሔርም ይህን ሰምቶ ተቈጣ፥**
**እስራኤልንም እጅግ ናቀ**
**60 የሴሎምን ማደሪያ ተዋት**
**በሰዎች መካከል ያደረገባትን ድንኳኑን**
**61 ኃይላቸውን ለምርኮ፥**
**ሽልማቱንም በጠላት እጅ ሰጠ።**
**62 ሕዝቡንም በጦር ውስጥ ዘጋቸው፥**

ርስቱንም ቸል አላቸው።
[63]ጕልማሶቻቸውን እሳት በላቸው፥
ቈነጃጅቶቻቸውም አላዘኑም
[64]ካህናቶቻቸውም በሰይፍ ወደቁ፥
ባልቴቶቻቸውም አላለቀሱላቸውም።

**78፥54-64** ይህ አንጓ የተስፋይቱን ምድር ድል መሆንና መቆርቆር (መኖርያ መሆን) ዳግም ይጠቅሳል (ዘፍ. 15፥12-21)። የከነአናውያን ነገዶች (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቅድመ-እስራኤላውያን የፍልስጥኤም ነዋሪዎች) በእግዚአብሔር ተሸንፈዋል ተወግደዋልም፣ በኃጢአታቸው ምክንያት። በሚያሳዝን መልኩ በእስራኤል ነገዶችም ላይ ተመሳሳይ ነገር ሆነ።

**78፥55ለ** መጽሐፈ-ኢያሱ፣ ምዕራፍ 12-19፣ የመሬቱን መለኮታዊ ክፍፍል ይገልጻል፣ ለያዕቆብ ልጆች።

**78፥56-58** እነዚህ የቅኔ ስንኞች የእስራኤልን ኃጢአትና ዓመጻ ይገልጻሉ፣ ይኸውም እጅግ የሚያስፈራ ነው፣ እግዚአብሔር ለእነርሱ ካደረገላቸው አኳያ (ሉቃስ 12፥48)።

1. እነርሱ እግዚአብሔርን ፈትነዋል፣ መዝ. 78፥56ሀ
2. እነርሱ በእግዚአብሔር ላይ ዓምጸዋል፣ መዝ. 78፥56ሀ
3. እነርሱ ኪዳኑን አልጠበቁም፣ መዝ. 78:56b
4. እነርሱ ጀርባቸውን አዞሩበት፣ መዝ. 78:57ሀ
5. እነርሱ እንደ አባቶቻቸው ከዱ፣ መዝ. 78:57ሀ
6. እንደ ጠማማ ቀስት ተገለበጡ፣ መዝ. 78:57ለ
7. በከነአናውያን አማልክት አስቆጡት፣ መዝ. 78:58ሀ
8. በተቀረጹ ምስሎቻቸውም አስቀኑት፣ መዝ. 78:58ለ

**78፥59-64** እነዚህ ቁጥሮች የሚገልጹት እግዚአብሔር በእስራኤላውያን ላይ ምን እንዳደረገ ነው፣ ከእነርሱ ድርጊት አኳያ (መዝ. 78፥56-58)።

1. እርሱ በቍጣ ተሞላ
2. እርሱ እስራኤልን እጅግ ተጸየፈ
3. እርሱ የሴሎን የማደሪያ ስፍራውን ተወ (1 ሳሙ. 4፥11)
4. እርሱ እስራኤል እንዲሸነፍ ተወው
5. እርሱ እስራኤልን ለሰይፍ አሳልፎ ሰጠ
6. እርሱ በርስቱ ላይ በቍጣ ተሞላ
   ሀ. እሳት ወጣት ልጆችን (ጎልማሶችን) በላ
   ለ. ቆነጃጅትም ሠርግ አልኖራቸውም
   ሐ. ካህናት ተገደሉ
   መ. መበለቶች አለቀሱ

የሰው ምርጫዎች ውጤት አላቸው፣ በሁለቱም በጊዜያዊውም ሆነ በዘላለማዊው!

**78፥62 "ርስቱ"** ይህ "የእርሱ ሕዝብ" ከሚለው ጋር ትይዩ ነው (መዝ. 106፥40)። የዚህ ምናባዊ ምስያ መነሻው ዘዳ. 9፥29 ነው። እሱም እንደ ብዙዎቹ ሌሌች ምስያዎች፣ ቤተሰብ-ተኮር ነው።

**78፥63 "እሳት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እሳት

## *መዝሙር ፡ 78፥65-72*

[65]እግዚአብሔርም ከእንቅልፍ እንደሚነቃ ተነሣ፥
የወይን ስካር እንደ ተወው እንደ ኃያልም ሰው
[66]ጠላቶቹንም በኋላቸው መታ
የዘላለምን ኀሣር ሰጣቸው።
[67]የዮሴፍንም ድንኳን ተዋት፥
የኤፍሬምንም ወገን አልመረጠውም
[68]የይሁዳን ወገን ግን መረጠ፥
የወደደውን የጽዮንን ተራራ።
[69]መቅደሱን እንደ አርያም ሠራ፥
ለዘላለምም በምድር ውስጥ መሠረታት።
[70]ዳዊትንም ባሪያውን መረጠው፥
ከበጎቹም መንጋ ውስጥ ወሰደው
[71]ከሚያጠቡ በጎችም በኋላ፥
ባሪያውን ያዕቆብን ርስቱንም እስራኤልን
ይጠብቅ ዘንድ ወሰደው።
[72]በልቡ ቅንነት ጠበቃቸው፥

|  |
|---|
| **በእጁም ብልሃት መራቸው።** |

**78፡65-72** ይህ የመደምደሚያ አንጓ የሚገልጸው እግዚአብሔር እንዴት ከቁጣው እንደሚመለስ ነው፣ ወደ መዋጀት ዕቅዱ ዓላማ ለመቀጠል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

1. እግዚአብሔር እንደ ሰው ተገልጿል፣ ወደ ስሜቱ እንደሚመለስ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሲገለጽ)
2. እርሱ የሕዝቦቹን ጠላቶች ድል ነሥቷል
3. እርሱ የዘላለም ተግዳሮት ሰጥቷቸዋል
4. እርሱ ድጋሚ አስታውቋል፣ የነገዶችን ቅደም ተከተል፣ እንደ አመራር ስፍራዎች
   ሀ. ዮሴፍንና ኤፍሬምን ትቷቸዋል
   ለ. የይሁዳን ነገድ መርጧል (ዘፍ. 49፡8-12፤ ዘዳ. 33፡7)
5. እርሱ መቅደሱ የሚሆንበትን ስፍራ መርጧል፣ በይሁዳ በሞሪያ ተራራ (ጽዮን በሚባለው)
6. እርሱም ዳዊትን መረጠ፣ እንደ ልዩ መሪ (የእርሱንም ዝርዮች፣ 2 ሳሙኤል 7)
   ሀ. እንደ እረኛ ተገልጿል
   ለ. ጽኑ ልብ አለው
   ሐ. የሠለጠኑ እጆች አሉት

እግዚአብሔር የሰሜኑን ነገዶች ትቶ ይሁዳን መምረጡ ከጠቃሽ ዘይቤነቱ አኳያ የሚመስለው የዚህ መዝሙር የመጨረሻ መልክ የተጻፈው ከእስራኤል/ኤፍሬም/ሰማርያ መውደቅ በኋላ ነው፣ በ722 ቅ.ል.ክ፣ ለሶርያ።

ይህ አንጓ የተሻለ ምሳሌ ነው፣ እግዚአብሔር ሉዓላዊነቱን እንዴት እንደሚያስረግጥ። ባህላዊው ተስፋ ተቀይሯል፣ የእግዚአብሔርን ተቆጣጣሪነት ለማሳየት።

1. ይሁዳ፣ ኤፍሬም ሳይሆን
2. ጽዮን፣ ሴሎ ሳይሆን
3. ዳዊት፣ ሌሎቹ የእሴይ ልጆች ሳይሆኑ

ይህም ከሥነ-መለኮት አኳያ ከአባቶች ጋር ተመሳሳይ ነው፣ ሁሉም መካን ሴቶች ማግባታቸው። ልጆቻቸው ከተፈጥሮ በላይ— ተፈጥሯዊ የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው። እርሱ ጊዜን፣ ስፍራን፣ ታሪክን፣ ምርጫን፣ እና ደኅንነትን ይቆጣጠራል!

# መዝሙር 79
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሰቆቃ ለኢየሩሳሌም ጥፋት እና ለዕርዳታ ጸሎት<br><br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>የአሳፍ መዝሙር | ሙሾና ጸሎት ለእስራኤል፣ በጠላቶች ለጠፋው | ከብሔራዊ ጠላት ለመታደግ ጸሎት | ጸሎት ለአገሩ ትድግና | ብሔራዊ ሰቆቃ |
| 79:1-7 | 79:1-7 | 79:1-4 | 79:1-7 | 79:1-2 |
| | | | | 79:3-5 |
| | | 79:5-7 | | |
| | | | | 79:6-7 |
| 79:8-13 | 79:8-10 | 79:8-10 | 79:8-10 | 79:8-9 |
| | | | | 79:10-11 |
| | 79:11-12 | 79:11-13 | 79:11-13 | |
| | | | | 79:12-13 |
| | 79:13 | | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 79፡1-7**

**1አቤቱ፥ አሕዛብ ወደ ርስትህ ገቡ**
**የቅድስናህንም መቅደስ አረከሱ፥**
**ኢየሩሳሌምንም እንደ መደብ አደረጉአት።**
**2የባሪያዎችህንም በድኖች ለሰማይ ወፎች መብል አደረጉ፥**
**የጻድቃንህንም ሥራ ለምድር አራዊት**
**3ደማቸውንም በኢየሩሳሌም ዙሪያ እንደ ውኃ አፈሰሱ፥**
**የሚቀብራቸውም አጡ።**
**4ለጎረቤቶቻችንም ስድብ ሆንን፥**
**በዙሪያችንም ላሉ ሣቅና ዘበት።**
**5አቤቱ፥ እስከ መቼ ለዘላለም ትቈጣለህ?**
**ቅንዓትህም እንደ እሳት ይነድዳል?**
**6ስምህን በማይጠሩ መንግሥታት ላይ**
**በማያውቁህም አሕዛብ ላይ መዓትህን አፍስስ**
**7ያዕቆብን በልተውታልና፥**
**ስፍራውንም ባድማ አድርገዋልና።**

**79፡1-3** እነዚህ ቁጥሮች የአሕዛብ ወራሪዎች በኪዳን ሕዝቦች ላይ ያደረጉትን ያሳያሉ (የተጠናቀቁዎች)።
1. ርስትህን ወረሩ ("ገቡ") — ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፤ ቃል የተጠናቀቀ
2. ቅዱስ መቅደስህን አረከሱ – ቢዲቢ 379፣ ኬቢ 375፤ ፒል የተጠናቀቀ
3. ኢየሩሳሌምን ፍርስራሽ አደረጓት ("ማስቀመጥ፣" "ስፍራ፣" "ማኖር") – ቢዲቢ 962፣ ኬቢ 1321፣ ቃል የተጠናቀቀ
4. የሞቱትንም በድኖች ሰጡ. . .ለሰማይ አዕዋፍ ምግብ – ቢዲቢ 678፣ ኬቢ 733፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ ኤር. 7:33፤ 16:4፤ 19:7፤ 34:20
5. ደማቸውንም አፈሰሱ – ቢዲቢ 1049፣ ኬቢ 1629፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 79:6፣ 10
6. የሚቀብራቸውንም አጡ – ቢዲቢ 868፣ ኬቢ1064፣ ቃል አንቀጽ

አይሁድ ፈጽሞ ሊገባቸው አልቻለም፣ አምላካቸው ምድራቸውን ለወራሪዎች ለምን አሳልፎ እንደሰጠና መቅደሱ እንዲረከስ እንደተወ (ማለትም፣ ዕንባቆም)። ይኸውም የእሱን የሚያጠይቅ ይመስላል፡
1. ኃይል
2. ተስፋዎች
3. ለእስራኤል ያለውን ዓላማ

መዝሙር 79፡8-13 ምላሹን ይሰጣል (ዳን. 9፡1-14)።

**79፡1 "አምላክ ሆይ"** ይህ ከበርካታ ተጠሪዎች መካከል የመጀመሪያው ነው።
1. አምላክ ሆይ (ኤሎሂም)፣ መዝ. 79፡1
2. ጌታ ሆይ (ያህዌ)፣ መዝ. 79፡5
3. አምላክ ሆይ (ኤሊዮን) መዝ. 79፡9
4. ጌታ ሆይ (አዶናይ)፣ መዝ. 79፡12

ኤቢ ሁለት ተጨማሪዎች ያክላል (ገጽ 249)።

5. አምላክ ሆይ፣ መዝ. 79፡6
6. ጸሐፊው ሆይ፣ መዝ. 79፡8

▣ **"ርስትህ"** መዝሙረኛው ምን ያህል ጊዜ አጽንዖት እየሰጠ እንደሚገልጽ ተገንዘብ፣ ጥቃቱ በያህዌ ላይ መሆኑን።
1. ርስትህ፣ መዝ. 79፡1
2. መቅደስህ፣ መዝ. 79፡1
3. ባሪያዎችህ፣ መዝ. 79፡2፣ 10
4. ለስምህ ክብር፣ መዝ. 79፡9
5. ስለ ስምህ ስትል፣ መዝ. 79፡9
6. ሕዝብህ፣ መዝ. 79፡13
7. የማሰማሪያህም በጎች፣ መዝ. 79፡13

▣ **"በፍርስራሽ"** ይህ የአልፎ አልፎ ቃል ነው (ቢዲቢ 730) እርሱም ሚክያስ ላይ ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ።
1. ለሰማርያ ጥፋት፣ ሚክ. 1፡6
2. ለኢየሩሳሌም ጥፋት፣ ሚክ. 3፡12 (ኤር. 26፡18 ላይ የተጠቀሰ)

ይህ መዝሙር የሚያንጸባርቀው የኢየሩሳሌምን መውደቅ ነው በናቡከደነፆር፣ በ586 ቅ.ል.ክ (2 ነገሥት 25፤ 2 ዜና መዋዕል 36 እና ሰቆቃወ ኤርምያስ ተመልከት)።

**79፡2** ያላግባብ የሆነ ቀብር ለጥቅም ሰዎች (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አሰቃቂ ነበር። በእንስሳት መበላት አስፈሪ ሁናቴ ነበር (ኤር. 7:33፤ 8:2፤ 34:20፤ ሕዝ. 29:5፤ 32:4-6፤ 33:27፤ 39:4-5፣17-20)። መዝሙር 79:2 ፍጻሜ ነው፣ ዘዳ. 28፡26 ላይ ያለው ላለመታዘዝ የሆነው ርግማን!

ልዩ ርዕስ፡ የቀብር ሥነ-ሥርዓቶች

**79፡3** የዚህ ቁጥር የመጀመሪያው መስመር የሚጠቅሰው የአምልኮ ሥርዓትን ነው፣ እዚያም የመሥዋዕቱ ደም ወደ መሥዋዕቱ መሠዊያ መሠረት የሚወርድበት፣ አነስተኛ መጠን ያለው ብቻ የመሠዊያውን ቀንድ ከሚሸፍነው በቀር (ማለትም፣ ሌዋ. 4፡7)። ኢየሩሳሌም እንደ አምልኮ መሥዋዕት ፈርሳለችና እናም የሙታኑ በድን ለዱር አራዊት እንደ ግብዣ።

**79፡4** የኪዳኑ ሕዝብ ሆነዋል
1. መሳለቂያ ("መዘባበቻ፣" ቢዲቢ 357) ለአሕዛብ ጎረቤቶቻቸው፣ መዝ. 44፡13፤ 69፡9፣19፤ 80፡6፤ 89፡41
2. መሳቂያ ("መቀለጃ፣" ቢዲቢ 541)፣ መዝ. 44፡13፤ ሕዝ. 23፡32፤ 36፡4
3. መቀለጃ፣ መዝ. 44፡13፤ ኤር. 20፡8 (ስም ፣ ቢዲቢ 887፣ ሦስት ጊዜ ብቻ ጥቅም ላይ የዋለ እንዲሁም የግሥ መልኩ አራት ተጨማሪ ጊዜ፣ ብኪ ላይ)

ይህም በትክክል ተቃራኒው ነው፣ እግዚአብሔር ለእስራኤል ካለው ዓላማ ጋር፣ ይኸውም አሕዛብ እንዲያውቁት እንዲረዱ እና ወደ እርሱ እንዲመጡ (ሕዝ. 36፡22-23)።

**79፡5** እነዚህ ሦስት ጥያቄዎች፣
1. እስከ መቼ? (መዝ. 13፡1፤ 74፡10፤ 80፡4፤ 89፡46፤ 90፡13፤ 94፡3)
2. እስከ ዘላለም ትቆጣለህን? (መዝ. 44፡23 74፡1፤ 77፡7፤ 85፡5፤ 89፡46)
3. ቅንዓትህስ ዝንደ እሳት ትነድዳለችን? (መዝ. 89፡46)

የእስራኤል ግራ መጋባትና ጸሎት ትኩረት ናቸው። ያህዌ ከአብርሃም ዝርያዎች ጋር የነበረው የተለየ ግንኙነት ተለወጠን (መዝ. 89፡1-4)?

ያህዌ የማይለወጥ ዓላማ ለእስራኤል አለው (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)፣ ነገር ግን እነርሱ ማስታወስ የሚኖርባቸው የጥበቃ፣ የመጋቢነት፣ እና የመገኘቱ ተስፋዎች ሁኔታዊ መሆናቸውን ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን)። እያንዳንዱ ትውልድ በኪዳኑ መታቀፍና መኖር አለበት። መዝሙራት የብኪ "ሁለቱ መንገዶች" ክፍል እንደሆኑ አስታውስ (ዘዳ. 30፡15-20፤ መዝሙር 1)።

**79፡6-7** ይህ ጸሎት ነው ("ማፍሰስ፣" ቢዲቢ 1049፣ ኬቢ 1629፣ *ቃል ተተኳሪ*) ለያህዌ፣ በፍርድና በማዳን ላይ እንዲሠራ (መዝ. 79፡9) ለኪዳን ሕዝቡ (ኤር. 10፡25)። አሕዛብ ባሕርያቸው (ቢዲቢ 156) እንዴት እንደተሳለ ተገንዘብ።

1. አንተን አያውቁህም (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ)
2. ስምህን አይጠሩም (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጥላ እንደ ዘይቤ፣ ለጥበቃና ለክብካቤ)

መታወስ የሚኖርበት አሕዛብ

1. እውነተኛ ራዕይ የላቸውም
2. በአጋንንታዊ ተመስጦ የባዕድ አምልኮ ጣዖታት ቁጥጥር ሥር ናቸው

እስራኤል እንዲሆን ታስቦ የነበረው የያህዌ መገለጥ መገናኛ መስመር እንዲሆን ነበር፣ ስለ ራሱ። አስገራሚ የማይሆነው አሕዛብ ተገቢ ባልሆነ መንገድ ማድረጋቸው ነው (መዝ. 79፡7)። አስገራሚ የሚሆነው እስራኤል፣ ከሁሉም መንፈሳዊ ጠቀሜታዎቿ አኳያ (ሮሜ. 9፡4-5)፣ በገዛ መንገዷ ማድረጓ ነው (ሉቃስ 12፡48)!

**79፡7 "እነርሱ አላቸውና"** ኤምቲ "እርሱ አለውና" የሚል አለው፣ ነገር ግን የጥንት ቅጅዎች "እነርሱ" የሚል ነው ያላቸው (LXX፣ ሶርያኛ፣ ቫልጌት)። ለውጡ የተያያዘው በዳግም አናባቢ (በድምጸት) ብቻ ነው።

▣

**አአመመቅ፣ አየተመቅ** **"መኖርያ"**
**አአመመቅ ኅዳግ** **"መሰማርያ"**
**አኪጀት** **"ማደርያ ሰፍራዎች"**
**አእቅ** **"አገር"**
**አኢመቅ፣ ጀፒኤስኦኤ** **"ቤት"**
**የተእመቅ** **"የትውልድ አገር"**

ይህ ሥር (ቢዲቢ 627) በርካታ ፍችዎች አሉት።

1. የእረኛ ማደሪያ (ማለትም፣ ኤር. 33፡12) ወይም የሰው (ማለትም፣ ኢዮብ 18፡15)
2. የሕዝብ መኖርያ (ማለትም፣ ኤር. 31፡23 – ይሁዳ፤ 49፡20 – ኤዶም፤ 50፡45 – ባቢሎን)
3. ከተማ (ኢሳ. 33፡20)
4. ራቅ ያሉ ወታደራዊ ሰፈሮች (ኒዶቲ፣ ቅጽ. 3፣ ገጽ. 55፣ ማለትም.፣ መዝ. 79፡7፤ ኢሳ. 27፡10፤ ኤር. 10፡25፤ 25፡30)
5. መኖርያ (ማለትም፣ ምድር፣ ኤር. 25፡30)
6. ማረፊያ ስፍራ (ቢዲቢ 628፣ ኢሳ. 32፡18 ትይዩ)

መዝሙር 79፡7 የቁ. 2ን አጠቃቀም ተከትሎ።

### መዝሙር ፡ 79፡8-13

**8የቀደመውን በደላችንን አታስብብን፥**
**ምሕረትህ በቶሎ ታግኘን፥**
**እጅግ ተቸግረናልና።**
**9አምላካችንና መድኃኒታችን ሆይ፥ እርዳን ስለ ስምህ ክብር፥**
**አቤቱ፥ ታደገን፥ ስለ ስምህም ኃጢአታችንን አስተሰርይልን።**
**10አሕዛብ፥ አምላካቸው ወዴት ነው? እንዳይሉ፥**
**የፈሰሰውን የባሪያዎችህን ደም በቀል**
**በዓይኖቻችን ፊት አሕዛብ ያወቁ**
**11የእስረኞች ጩኸት ወደ ፊትህ ይግባ**
**እንደ ክንድህም ታላቅነት ሊገደሉ የተፈረደባቸውን አድን።**
**12አቤቱ፥ የተዘባበቱብህን መዘባበታቸውን**
**ለጎረቤቶቻችን ሰባት እጥፍ በብብታቸው ክፈላቸው።**
**13እኛ ሕዝብህ ግን፥ የማሰማርያህም በጎች፥**
**ለዘላለም እናመሰግንሃለን**
**ለልጅ ልጅም ምስጋናህን እንናገራለን።**

**79፡8-9** ሁለት ጠቃሚ ጉዳዮች ከእነዚህ ቁጥሮች ይወጣሉ።

1. የእስራኤል ጸሎት ለእግዚአብሔር፣ ኪዳኑን እንዲያስታውስ
2. የእስራኤል ጸሎት ለእግዚአብሔር፣ በቀጣይነት ያደረጉትን የኪዳን ዓመጻ እና አለመታዘዝ እንዳያስታውስ

የጸሎታቸው መሠረት ያደረጉትም አሕዛብ ያህዌን ያላግባብ እንዳይረዱት በሚለው ሐቅ ላይ ነው (መዝ. 79፡10)።

እነዚህ ሁለት ቁጥሮች አራት የአስቸኳይ ጥያቄ ተተኳሪዎች እና ሁለት ያልተጠናቀቁ አሏቸው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ።

1. አታስታውስ – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*

2. ፈጥነህ ና – ቢዲቢ 554፣ ኬቢ 553፣ ፒል ተተኳሪ
3. ልትገናኘን – ቢዲቢ 869፣ ኬቢ 1068፣ ፒል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
4. ዕርዳን – ቢዲቢ 740፣ ኬቢ 810፣ ቃል ተተኳሪ
5. አድነን – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ ሂፊል ተተኳሪ
6. ኃጢአታችንን ይቅር በለን – ቢዲቢ 497፣ ኬቢ 493፣ ፒል ተተኳሪ

**79፡8** መስመር 1 የኃጢአት መሸጋገር ሥነ-መለኮታዊ ጉዳይ ጠቃሽ ነው (እና/ወይም ባርኮት/ይቅርታ) ለቀጣዩ ትውልድ። በአስርቱ ቃላት

1. የኃጢአት ውጤት እስከ ሦስተኛና አራተኛ ትውልድ ድረስ ይጎበኛል (ዘጸ. 20፡5፤ ዘዳ. 5፡9)
2. ምሕረትም ለብዙ ትውልድ፣ ያህዌን ለሚወዱና ትእዛዙን ለሚጠብቁ፣ ለእነርሱ (ዘጸ.34:7፤ ዘዳ. 5:10፤ 7:9)

ሁለቱም የኃጢአት ውጤትና ምሕረት በጊዜ ውስጥ ይሆናሉ፣ ነገር ግን እያንዳንዳቸው የሚመሠረቱት በሰዎች ምርጫ ላይ ነው!

**79፡9 "አምላካችንና መድኃኒታችን ሆይ፥"** ይህ ሐረግ የተደገመ መጠሪያ ነው፣ ለእስራኤል አምላክ (መዝ. 18:46፤ 24:5፤ 25:5፤ 27:9፤ 65:5፤ 85:4)።

ቢዲቢ በርካታ መንገዶችን ይዘረዝራል፣ "ደኅንነት" ለሚለው ቃል (ቢዲቢ 447) ብኪ ላይ ጥቅም ላይ የዋሉትን።

1. ሴቴ (አንስታይ)
   ሀ. ጠቀሜታ፣ ብልጽግና
   ለ. ማዳን
   ሐ. ከውጫዊ ክፉዎች መዳን (ማለትም፣ መዝ. 78:22፤ 80:2)
   መ. ድል (ማለትም፣ መዝ. 20:5፤ 21:1፣5፤ 44:4)
2. ወንዴ (ተባዕታይ)
   ሀ. ደኅንነት፣ ጠቀሜታ፣ ብልጽግና (ማለትም፣ መዝ. 12፡5)
   ለ. ደኅንነት (እዚህጋ ያለው አጠቃቀም)
   ሐ. ድል (ማለትም፣ መዝ. 20፡6)

**79፡10-13** ሁለቱን ዓይነት ሕዝብ ተገንዘብ (ማለትም፣ እስራኤላውያን — አሕዛብ)። አሕዛብ ስለ ያህዌ አላዋቂዎች ናቸው እናም ተገቢ ባልሆነ መንገድ ነው የሚያደርጉት። እስራኤል ፍርድን ይለምናል፣ ሕዝቡ

1. "ምስጋና ያቀርቡ" ዘንድ – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ
2. "ምስጋናህን ይናገሩ" ዘንድ – ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765፣ ፒል ያልተጠናቀቀ

የመዝሙረኛውን ሥቃይ መመልከት አስደንጋጭ ነው፣ በኢየሩሳሌም መውደቅ፣ በመቅደሱ መርከስ፣ እና በዳዊት ዘር ስደት ላይ። ሆኖም፣ በእምነት፣ የወደፊቱን ምስጋና አሁንም መመልከት ችሏል!

**79፡10 "አምላካቸው ወዴት ነው?"** አሕዛብ ብርቱ ጥያቄ ጠይቀዋል (መዝ. 42:3፣10፤ 115:2)። መዝሙር 42 ላይ እሱ በሌሎች እስራኤላውያን ተጠይቋል፣ ነገር ግን መዝሙር 115 እና እዚህ ጋ በአሕዛብ ነው። እነርሱ መረጃ እየፈለጉ ወይስ በእስራኤል አምላክ እያሾፉ ነውን? ሁለተኛው አማራጭ ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ ግልጽ ነው፣ ነገር ግን የመጀመሪያው አማራጭ የእግዚአብሔር የመዳረሻ ዓላማ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

**79፡11 "ሊገደሉ የተፈረደባቸውን"** ይህ ያልተዘወተረ ሐረግ ነው (መዝ. 102፡20)። እሱም ሊያመለክት የሚችለው

1. ከወረራው ግዞት የተረፉት
2. ሞትን የሚጠባበቁት
3. ከመቅደስ የተከለከሉት (ጄፒኤስኦኤ የግርጌ ማስታወሻ፣ መዝ. 79፡13)

**79፡12 "ሰባት እጥፍ"** ሰባት ቁጥር ዘወትር የሚያመለክተው "ፍጽምናን" ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተምሳሌታዊ ቁጥሮች፣ በቅዱስ ቃሉ) እዚህጋ ግን የሚያመለክተው ፍጹም ፍርድን ነው (ዘዳ. 28:25፤ መዝ. 12:6፤ ምሳ. 6:31) (ዘጽ. 4:15፣24)።

▣ **"ወደ ብብታቸው"** "ብብት" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 300) በብዙ መልኩ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ጥቅም ላይ የዋለው። እዚህጋ የሚጠቅሰው የሰውን ውስጠኛ ክፍል ነው (መዝ. 35:13፤ ኤር. 32:18)። መዝሙረኛው ፍጹም ፍርድ እየለመነ ነው፣ በወራሪዎቹ አሕዛብ ላይ (ማለትም፣ ኢሳ. 65:6፣7)።

▣ **"የተዘባበቱብህን መዘባበታቸውን"** ስሙ እና ግሡ "መዘባበት" ወይም "ማሾፍ" (ቢዲቢ 357፣ መዝ. 74:10፣18 እና ተመሳሳይ ሥር መዝ. 74:22 ላይ፤ ሰቆ. 3:30፣61፤ 5:1) ዘወትር በቅዱስ ቃሉ ጥቅም ላይ ይውላል። መዝሙረኛው በኢየሩሳሌም ላይ የሚሆን ጥቃት በያህዌ ላይ እንደተደረገ ጥቃት ነው።

**79፡13 "የማሰማርያህም በጎች፥"** አስገራሚ የሚሆነው በአሳፍ መዝሙር ላይ ይህ ጭብጥ መዝሙር 77፣ 78፣ እና 79 ላይ መደምደሚያ መሆኑ ነው (እንዲሁም መዝሙር 80 እንዴት እንደሚጀምር ተመልከት)። እርሱም ብርቱውን፣ ግላዊውን እውነት/ምናብ ያንጸባርቃል፣ የመዝሙር 23ን!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. 586 ቅ.ል.ክ የዚህ መዝሙር እጅግ የተሻለ ታሪካዊ መቼት ለመሆን ተገመተ?
2. እግዚአብሔር በሕዝቡ ላይ ለምን ተቆጣ? በዚህ መዝሙር ላይ የእርሱ ሕዝቦች እነማናቸው?
3. ኃጢአት ወደ ትውልድ ይዞራልን?
4. መዝ. 79፡10 ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ የመዋጀት ዓላማ ጋር እንዴት ይዛመዳል? (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።
5. መዝ. 79፡12ለ ከ ይቅርታና ከማዳን ጸሎት ጋር እንዴት ይዛመዳል?

# መዝሙር 80
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| አምላክ ይለመናል፣ ሕዝቡን ከጥፋት ያድን ዘንድ <br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ<br>የአሳፍ መዝሙር | ጸሎት ስለ እስራኤል መመለስ | ከብሔራዊ ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት | ጸሎት ስለ ሕዝብ መመለስ | ጸሎት ስለ እስራኤል መመለስ |
| 80:1-3 | 80:1-2 | 80:1-2 | 80:1-2 | 80:1-2 |
| | 80:3 | 80:3 | 80:3 | 80:3 |
| 80:4-7 | 80:4-6 | 80:4-6 | 80:4-6 | 80:4-6 |
| | 80:7 | 80:7 | 80:7 | 80:7 |
| 80:8-13 | 80:8-11 | 80:8-13 | 80:8-15 | 80:8-9 |
| | | | | 80:10-11 |
| | 80:12-13 | | | 80:12-13 |
| 80:14-19 | 80:14-18 | 80:14-18 | | 80:14-16 |
| | | | 80:16-18 | |
| | | | | 80:17-18 |
| | 80:19 | 80:19 | 80:19 | 80:19 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. የእስራኤልን አምላክ የተለያዩ ስሞች/መጠሪያዎች ተመልከቱ።
1. የእስራኤል እረኛ፣ መዝ. 80፡1 (መዝ. 23፡1)
2. አምላክ ሆይ (ኤሎሂም)፣ መዝ. 80፡3
3. ጌታ (ያህዌ)፣ መዝ. 80:4፤19
4. የሠራዊት ጌታ መዝ. 80:4፤7፤14፤19

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

ለ. አዝማች ሐረግ አለ፣ በርካታ አንጓዎችን የሚያካትት፡ መዝ. 80:1-3፤ 4-7፣ 14-19። እሱም ሁለት ተተኳሪዎች እና አንድ ተጓዳኝ አሉት። እሱም የምሕረት፣ ይቅርታ፣ እና የመመለስ ጸሎት ነው።

ሐ. “መሲሐዊ” ማጣቀሻ ይኖራል፣ የሚዛመደውም
1. “ቡቃያ” (ቢዲቢ 488)፣ ይኸውም ከ “ቅርንጫፍ” ጋር ሥነ-መለኮታዊ መያያዝ ያለው (ቢዲቢ 666፣ ኢሳ. 4:2፤ 11:1፤ 53:2፤ ኤር. 23:5) እና ለ “ቡቃያ” (ቢዲቢ 855፣ ኤር. 33:15፤ ዘካ. 3:8፤ 6:12)
2. “የቀኝህ ሰው”
3. “የሰው ልጅ እሱንም ለራስህ ብርቱ ያደረግከው”

4. እናም "የእስራኤል ጠባቂ" ይሆናል፣ ይኸውም የዳዊት ዘር ፍችን ሊያመጣ የሚችል
ሌላው አማራጭ የሚሆነው ሁሉም ምስያ ከብሔረ-እስራኤል ወይም ይሁዳ ጋር መያያዙ ነው።

መ. ከዚህ መዝሙር አቀማመጥ የተነሣ (ማለትም፣ በአሳፍ መዝሙር ውስጥ) እና መዝ. 80፡12-13 ወደ ይሁዳ መወረር ያመለክታል፣ ቀኑም ሊሆን የሚችለው 586 ቅ.ል.ክ ነው።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 80፡1-3**

[1]**ዮሴፍን እንደ መንጋ የምትመራ፥**
**የእስራኤል ጠባቂ ሆይ፥ አድምጥ**
**በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ፥ ተገለጥ።**
[2]**በኤፍሬምና በብንያም በምናሴም ኃይልህን አንሣ**
**እኛንም ለማዳን ና።**
[3]**አቤቱ፥ መልሰን፥**
**ፊትህንም አብራ፥ እኛም እንድናለን።**

**80፡1-3** ይህ አንጓ የተበጀው በተለጣጣቂ ተተኳሪ ጥያቄዎች ነው።

1. ስማ፣ መዝ. 80፡1 – ቢ.ዲ.ቢ. 24፣ ኬቢ. 27፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
2. አብራ፣ መዝ. 80፡1 – ቢ.ዲ.ቢ. 422፣ ኬቢ. 424፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
3. አንቀሳቅስ፣ መዝ. 80:2 – ቢ.ዲ.ቢ. 734፣ ኬቢ. 802፣ *ፖለል ተተኳሪ*
4. ለማዳን ና፣ መዝ. 80:2 – ቢ.ዲ.ቢ. 229፣ ኬቢ. 246፣ *ቃል ተተኳሪ*
5. መልሰን፣ መዝ. 80:3 – ቢ.ዲ.ቢ. 996፣ ኬቢ. 1427፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
6. አብራ፣ መዝ. 80:3 – ቢ.ዲ.ቢ. 21፣ ኬቢ. 24፣ *ሂፊል ተተኳሪ* (ይህ የአሮናዊ ባርኮትን የሚያንጸባርቅ ይመስላል፣ ዘኍ. 6:25 ላይ ያለውን፣ ደግሞም መዝ. 31:16 ላይ ያለው ማስታወሻ)
7. እንድናለን፣መዝ. 80:3 – ቢ.ዲ.ቢ. 446፣ 448፣ *ኒፋል ተጓዳኝ*

**80፡1 "የእስራኤል ጠባቂ"** ይህ ሐረግ የእግዚአብሔርን መገኘትና ርኅራኄአዊ ክብካቤ ያሳያል (ዘፍ. 49:24፤ መዝ. 23:1-3) እና ደግሞ ከዳዊት ጋር ይያያዛል፣ እርሱም በጎችን ከመጠበቅ በእግዚአብሔር የተጠራ። ይህም መሲሐዊውን ጠቃሽ የመሆን ዕድል መዝ. 80፡15-17 ላይ እጅግ ያልቀዋል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፣ ሐ)።

የእግዚአብሔርን ባሕርያት ተገንዘብ።

1. ዮሴፍን እንደ መንጋ የምትመራ (ዮሴፍ ደግሞ ተጠቅሷል መዝ. 77፡15፤ 78፡67 ላይ)
2. በኪሩቤል ላይ የምትቀመጥ። ይህ የዘጸ. 25፡22 ጠቃሽ ነው። ያህዌ በተምሳሌታዊነት በኪዳኑ ታቦት በምሕረት መከደኛው ላይ ይኖራል፣ በሁለቱ ኪሩቤል መካከል (1 ሳሙ. 4፡4፤ 2 ሳሙ. 6፡2፤ መዝ. 99፡1)። ይህ ሰማይና ምድር የሚገናኙበት ነበር በምሕረት እና በመገለጥ ስፍራ!

ለ "*ኪሩቤል*" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ *ኪሩቤል*።

▣ **"ያበራል"** ይህ አጽንዖት፣ በእግዚአብሔር በምድራዊ፣ በዕለታዊ ጉዳዮች ላይ ለእስራኤል እጁን ማስገባቱ ከታቦቱ ከላይ እንደሚመጣ መብራት ነው የተገለጸው። በዚህ መዝሙር ላይ ያለውን አዝማች ተገንዘብ (መዝ. 80:3፣7፣19) ሌላ ተተኳሪ ግሥ እንዳለው (ቢ.ዲ.ቢ. 21፣ ኬቢ. 24) ብርሃንን የሚገልጽ። ብርሃን በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) የራዕይ፣ የጤና፣ የደኅንነት ተምሳሌት ነው። በብኪ. እሱ ዘወትር የሚዛመደው ከቲዎፋኒ ብሩኅነት ጋር ነው (የእግዚአብሔር አካላዊ መከሰት)። መዝ. 50፡2፤ 94፡1ን ተመልከት፣ እንዲሁም ሼኪናህ የክብር ደመና፣ በዘጸአት ጊዜ እና በምድረ-በዳ የመንከራተት ዘመን (ማለትም፣ ዘጸ. 13:21-22፤ 33:9)።

እግዚአብሔር ብርሃን ነው – መዝ. 27:1፤ ኢሳ. 60:20፤ ሚኪ. 7:8፤ ያዕቆብ 1:17፤ 1 ዮሐንስ 1:5
ኢየሱስ ብርሃን ነው – ኢሳ. 9:2፤ ዮሐንስ 1:4፤ 8:12፤ 12:35፣46
አማኞች ብርሃን ናቸው – ማቴ. 5:14-16፤ ዮሐንስ 8:12ለ

**80፡2** አንዳንድ ጥያቄዎች አሉ፣ እነዚህ ነገዶች ብቻ ለምን እንደተጠቀሱ። ከዘኍ. 2፡18-24 እንደምንረዳው እነርሱ የሰፈሩት አንድ ላይ ነው፣ ከማደሪያው ድንኳን በስተምዕራብ በኩል፣ በምድረ-በዳ እየተጓዙ ሳለ።

ኤፍሬምና ምናሴ የዮሴፍ ልጆች ናቸው። ዮሴፍና ብንያም የያዕቆብ ተወዳጅ ሚስት የራሔል ልጆች ናቸው።

የዮሴፍ ልጆች ሙሉ ለሙሉ የያዕቆብ ማደጎ ልጆች ሆነዋል (ማለትም፣ አስራ ሦስት ነገድ) እናም ትልቁ ነገድ ሆነ፣ የተባበረው መንግሥት (ማለትም፣ ሳኦል፣ ዳዊት፣ ሰሎሞን) በ922 ቅ.ል.ክ ሲከፋፈል። እነርሱም የሰሜኑ ኅብረት መሪዎች ሆኑ፣ እስራኤል፣ ሰማርያ፣ ወይም ኤፍሬም ተብሎ የሚጠራው። የመጀመሪያው መሪ/ንጉሥ ኤፍሬማዊ ወገን መሪ፣ ይሮብአም 1።

ቢንያም የደቡብ ኅብረት፣ የይሁዳ አካል ሆነ፣ ከአብዛኛቹ ሌዋውያን ጋር። ስምዖን ቀደም ብሎ ከይሁዳ ጋር ተካትቷል፣ ስለዚህ፣ እሱ ሁሉንም የኪዳን ሕዝቦች መጥቀሻ መንገድ ይሆናል።

**80፡3** ይህ አዝማች (መዝ. 80፡7፣19) የሚያሳየው ይህ መዝሙር የተጻፈው በብሔራዊ ችግር ጊዜ እንደነበር ነው። መዝሙር 77-80 በአሳፍ ከተመሳሳይ ታሪካዊ ጊዜ ከመጣ፣ እንግዲያውስ ይህ መዝሙር ሊዛመድ የሚችለው ከይሁዳ በባቢሎን መወረር ጋር ነው፣ በናቡከደነጾር። እሱ በርካታ ጊዜ ወርሯል (ማለትም፣ 605፣ 597፣ 586፣ 582 ቅ.ል.ክ)፣ ነገር ግን ሊሆን የሚችለው ይህ መዝሙር ከእስራኤል መውደቅ ጋር እንደሚዛመድ አድርጎ መመልከት ይቻላል፣ በ722 ቅ.ል.ክ፣ ሰማርያ በወደቀችበት ጊዜ፣ ከሦስት ዓመት የሶርያ ከበባ በኋላ የአይሁድ የጥናት

መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ. 1372) የሚለው እሱ በመጀመሪያ የተጻፈው ለሰማርያ ውድቀት ነው፣ ነገር ግን እንደገና ተሠርቷል፣ የኢየሩሳሌም መውደቅን ለማመልከት ምክንያቱም ከተቀራራቢነትና ሐረጋዊ መያያዝ አኳያ፣ ከመዝሙር 79 ጋር፣ እሱም በግልጽ 586 ቅ.ል.ክ።

መዝ. 80፡14 አንድ ዓይነት ተተኳሪ ከመጠቀሙ የተነሣ (ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427)፣ አንዳንድ ሊቃውንት እሱን የሚመለከቱት እንደ ተጨማሪ አዝማች ነው፣ እናም እያንዳንዱ አንጓ የሚዘጋው በተመሳሳይ ነው። ሆኖም፣ መዝ. 80፡14 አንድ ዓይነት አይደለም፣ ተመሳሳዩ ግሥ እንኳ ቃል ነው እንጂ ሂሬል አይደለም።

**መዝሙር ፡ 80፡4-7**

**[4]የሠራዊት አምላክ አቤቱ፥**
**በባሪያህ ጸሎት ላይ እስከ መቼ ትቈጣለህ?**
**[5]የእንባ እንጀራን ትመግበናለህ፥**
**እንባም በስፍር ታጠጣናለህ።**
**[6]ለጎረቤቶቻችን ክርክር አደረግኸን፥**
**ጠላቶቻችንም በላያችን ተሣለቁብን።**
**[7]የሠራዊት አምላክ አቤቱ፥ መልሰን፥**
**ፊትህንም አብራ፥ እኛም እንድናለን።**

**80፡4-7** ይህ አንጓ ለእግዚአብሔር ልመና ነው፣ ለእርሱ ሕዝብ ብሎ ጣልቃ እንዲገባ።

1. እስከ መቼ ትቆጣለህ — የእግዚአብሔር ድርጊት እንዲሆን ወይም እንዳይሆን መጠየቅ ተደጋጋሚ ነው (መዝ. 74:10፤ 90:13፤ 94:3፤ ምሳ. 1:22)
2. የዕንባ እንጀራን ትመግባቸዋለህ (ብርቱ ምስያ ምናባዊ፣ መዝ. 42፡3፤ 102፡9)
3. ዕንባንም በስፍር እንዲጠጡ አደረግካቸው ("ሦስተኛ ከፋይ፣" ቢዲቢ 1026 I፣ እዚህጋ ብቻ እና ኢሳ. 40:12 ላይ)
4. ለጎረቤቶቻችንም ክርክር አደረግከን (መዝ. 44:13፤ 79:4፤ ሕዝ. 5:14፤ 22:4፤ ዳን. 9:16)
5. ጠላቶቻችንም እንዲሳለቁ አደረግክ (በእኛ ላይ)። አእቅ እና አኢመቅ "ጠላቶቻችን ተሳለቁብን" የሚለውን LXX፣ ይከተላሉ።

እነዚህ የእስራኤል/ይሁዳ የኪዳን አለመታዘዝ እና የጣኦት አምልኮ ውጤቶች በትክክል ተቃራኒዎች ናቸው፣ እግዚአብሔር እንዲያደርጉ ከሚፈልገው፣ ከአሕዛብ ጎረቤቶቻቸው፣ ከጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ)። እነርሱ ማለት ብርሃን እንዲሆኑ ነበር (ሕዝ. 36:22-23) ነገር ግን ቀልድ ሆኑ (መዝ. 79:10፤ 115:2)።

**መዝሙር ፡ 80፡8-13**

**[8]ከግብጽ የወይን ግንድ አመጣህ**
**አሕዛብን አባረርህ እርስዋንም ተከልህ።**
**[9]በፊትዋም ስፍራን አዘጋጀህ፥**
**ሥሮችዋንም ተከልህ ምድርንም ሞላች።**
**[10]ጥላዋ ተራሮችን ከደነ፥**
**ጫፎችዋም እንደ እግዚአብሔር ዝግባ ሆኑ።**
**[11]ቅርንጫፎችዋንም እስከ ባሕር፥**
**ቡቃያዋንም እስከ ወንዙ ዘረጋች።**
**[12]አጥርዋን ለምን አፈረስህ?**
**መንገድ አላፊም ሁሉ ይቀጥፋታል።**
**[13]የዱር እርያ አረከሳት፥**
**የአገር አውሬም ተሰማራባት።**

**80፡8-13** ይህ አንጓ የወይን ማሳን ለኪዳኑ ሕዝብ እንደ ዘይቤ ይጠቀማል።

1. ያህዌ እነርሱን ከግብፅ አወጣቸው (ዘፍ. 15፡12-21 ላይ ቃል እንደገባው)
2. ያህዌ የከነአንን ነገዶች አሸነፈ (ማለትም፣ የኢያሱ ድል)
3. ያህዌ በመልካም ምድር በተስፋይቱ ምድር ላይ ተከላቸው

በእነዚህ ሁሉ መለኮታዊ ባርኮቶች እንኳ ቢሆን እነርሱ ታማኞች አልነበሩም (ነህምያ 9፤ መዝሙር 78)። ስለዚህ የሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30 ርግማን ሆነ።

1. የእርሱ ጥበቃ (ማለትም፣ የወይን ማሳው ቅጥር) ተወገደ
2. እርሱ ለወራሪዎች ፈቀደላቸው ከነአንን ይወስዱ ዘንድ (መዝ. 80፡12-13)። እስራኤላውያን ኃጢአተኞቹን ከነአናውያንን እንዳስወጡ (ማለትም፣ ዘፍ. 15፡12-21) እንዲሁ ደግሞ አሁን ኃጢአተኞቹ የኪዳን ሕዝቦች ተወገዱ።

**80፡8 "ወይን"** ይህ የሚያመለክተው ሁሉንም የኪዳን ሕዝቦች ነው (ኢሳይያስ 5፤ ሆሴዕ 10፡1) ወይም የተለየ ማጣቀሻ ለሰሜኑ መንግሥት (ዘፍ. 49፡22)።

**80፡11 "ባሕር... ወንዝ"** ይህ የሚያመለክተው ሜዲትራኒያንን ነው፣ ወደ ምዕራብ ሲል፣ እንዲሁም የኤፍራጥስ ወንዝን መነሻ ውኃ፣ ወደ ሰሜናዊ ምስራቅ ሲል (ዘጸ. 23፡31)።

**መዝሙር ፡ 80፡14-19**

[14]የሠራዊት አምላክ ሆይ፥ እንግዲህ ተመለስ
ከሰማይ ተመልከት፥ እይም፥ ይህችንም የወይን ግንድ ጐብኝ።
[15]በሰው ልጅ ለአንተ ያጸናኸውን
ቀኝህ የተከላትን አንሣ።
[16]በእሳት ተቃጥላለች ተነቅላማለች
ከፊትህ ተግሣጽም የተነሣ ይጠፋሉ።
[17]ለአንተ ባጸናኸው በሰው ልጅ ላይ፥
በቀኝህ ሰው ላይ እጅህ ትሁን።
[18]ከአንተም አንራቅ
አድነን ስምህንም እንጠራለን።
[19]የሠራዊት አምላክ አቤቱ፥ መልሰን፥
ፊትህንም አብራ፥ እኛም እንድናለን።

**80፡14-19** ይህ አንጓ የማጠቃለያ ጸሎት ነው (3 *ቃል* የጥያቄ ተተኳሪዎች መዝ. 80፡14 ላይ) ለያህዌ በአብርሃም ዝርያዎች ላይ ምሕረቱን እንዲያደርግ።

የትርጓሜው ርግጠኛ ጥያቄ እነርሱ መለኮታዊው ድርጊት እንዴት እንደሚከሰት እንደሚመለከቱ ነው።

1. ጠንካራ መንግሥትን መልስልን (ማለትም፣ ቡቃያ [ቢዲቢ 488፣ እዚህጋ ብቻ ብኪ ላይ] ወይም ወይን መዝ. 80፡8፣14 ላይ ያለው)
2. የተለየ የዳዊት ዘርን ላክ (መዝ. 80፡15፣17)
   ሀ. አንተ ባጸናኸው ወይም በጠበቅከው ልጅ (ቢዲቢ 54)
   ለ. እጅህ ባጸናችው ሰው፣ ቀኝህም፣ አንተ ባጸናኸው የሰው ልጅ ላይ (ቢዲቢ 54፣ ከመዝ. 80፡15 ጋር ትይዩ) ለራስህ (መዝ. 110፡1)

ይህ ምስያ ምን እንደሚጠቅስ ግልጽ ነው

1. ብሔረ እስራኤልን/ይሁዳን
2. ዳዊታዊ ንጉሥ/መሲሕ (2 ሳሙኤል 7 እና አራማዊ ታርጉምስ)

**80፡16** የእስራኤል/ይሁዳ አስቸጋሪ ሁኔታዎች የእግዚአብሔር ድርጊቶች ቀጥተኛ ውጤቶች እንደሆኑ ተገንዘብ፣ የወራሪው ኃይል ሳይሆን። እግዚአብሔር ጣዖት አምላኪ አሕዛብን ተጠቅሟል በሕዝቡ ላይ ለመፍረድ (ዕንባቆም)። ይህም ለአይሁድ ሕዝብ አስደንጋጭ ነበር። እርሱ በእነርሱ ጎን ተዋግቶ ነበር (መዝ. 76፡6) አሁን ግን በወራሪዎች በኩል ሆኗል (ማለትም፣ "የቅዱስ ጦርነት" የተገላቢጦሽ ምናባዊ ምስያ)።

**80፡17 "እጅህ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ

▣ **"የሰው ልጅ"** ይህ ሐረግ ሕዝቅኤል ላይ ተደጋጋሚ ነው። ከታች ያለውን የእኔን ሐተታ (ኮሜንተሪ) ማስታወሻ ተመልከት፣ ከሕዝቅኤል 2፡1 ላይ።

> **ሕዝ. 2፡1 "የሰው ልጅ"** ይህ በጥሬው "ቤን-አዳም" ነው (ቢዲቢ 119 አወቃቀር፣ ቢዲቢ 9)። ይህም ሕዝቅኤል ላይ ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል፣ ሕዝቅኤልን እንደ የሰው ልጅ ለማመልከቻ መንገድ (93 ጊዜ፣ መዝ. 8፡4)። ሕዝቅኤል ላይ እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን የሚናገርበት መንገድ ነው። ይኸው ተመሳሳይ ሐረግ ኢዮብና መዝሙር ላይ ይገኛል። ዳን. 7፡13 ላይ ይህ ቃል መለኮታዊ ባሕርይ ይይዛል "የሰው ልጅን" ለሚመስለው፣ ከዘመናት በፊት እንደመጣ (ማለትም፣ መለኮት) በሰማይ ደመና ተቀምጦ። ዳንኤል 7፡13 ኢየሱስ ይሄንን ቃል ስለ ራሱ በዳራነት የተጠቀመበት ነው፣ እሱም ሰውነትን ከመለኮትነት ጋር ያዋሀደበት (ማለትም፣ 1 ዮሐንስ 4፡1-3)። ሐረጉ ምንም ዓይነት ብሔራዊነት ወይም ወታደራዊ ራቢያዊ ድርብ ፍች የለውም።

**80፡18** ይህ ሐረግ በርካታ ተስፋዎችን ይዘረዝራል፣ በመዝሙረኛው የተባሉትን፣ ነገር ግን ከኪዳኑ ሕዝብ አኳያ።

1. ከዚያም (ማለትም፣ እግዚአብሔር ወደ እነርሱ ዳግም ከተመለሰ በኋላ፣ መዝ. 80፡14) ወደ ኋላ አንመለስም (ማለትም፣ ውድቀት፣ ቢዲቢ 690፣ ኬቢ 744፣ *ቃል*፣ ያልተጠናቀቀ) ከአንተ
2. ሕይወትን ስጠን/መልሰን (ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ ፒይል ያልተጠናቀቀ)
3. እግዚአብሔር ከእነርሱ ጎን ከሠራ፣ እነርሱ ይጠራሉ (ቢዲቢ 894፣ ኬቢ 1128፣ *ቃል*፣ ያልተጠናቀቀ) ስሙን በመቅደስ

ያልተጠናቀቁትን አጠቃቀም ተገንዘብ፣ እነርሱም ቀጣይነት ያለውን ድርጊት እንደሚገልጹ።

**80፡19** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 80፡3 ላይ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር የሚገልጸው ወረራን ነውን? እንደዛ ከሆነ፣ የትኛው ታሪካዊ መቼት በተሻለ ይሰማማዋል?
2. ይህ መዝሙር የተጻፈው ስለ እስራኤል ነው ወይስ ይሁዳ?
3. የ "ብርሃንን" የተለያዩ ቃላት እና ጠቃሾችን ዘርዝር፣ አብራራም።
4. የመዝ. 80፡3፣7፣19 አዝማች በእግዚአብሔር ስም ላይ በየጊዜው ለምን ይጨመራል?
5. አሕዛብ ለተክል ዘይቤ ለምን ዘወትር ይጠቀሳሉ?
6. "መሲሐዊ" ጥቆማዎች በዚህ መዝሙር ላይ ይኖራሉን፣ ወይስ እነርሱ ሁሉ የተጠቀሱት ባጠቃላይ ለአሕዛብ ነውን?

# መዝሙር 81
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር መልካምነት እና የእስራኤል አስቸጋሪነት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ በጌቲዝ የአሳፍ መዝሙር | ልመና ለእስራኤል ንስሐ | የበዓል የአምልኮ ሥርዓት | የበዓል መዝሙር | ለዳስ በዓል |
| 81:1-5 | 81:1-2 | 81:1-5ለ | 81:1-5ለ | 81:1 |
| | | | | 81:2-3 |
| | 81:3-5 | | | |
| | | | | 81:4-5ለ |
| | | 81:5ሐ-10 | 81:5c-10 | 81:5ሐ-7ሀ |
| 81:6-10 | 81:6-7 | | | |
| | | | | 81:7ለ-8 |
| | 81:8-10 | | | |
| | | | | 81:9-10 |
| 81:11-16 | 81:11-12 | 81:11-16 | 81:11-16 | 81:11-12 |
| | 81:13-16 | | | 81:13-14 |
| | | | | 81:15-16 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ብዙ ክርክር አለ፣ ይሄ የሚጠቅሰው የዳስ በዓልን ወይም ፋሲካን እንደሁ።

ለ. ታርጉም ቲሽሪ (*Tishri*) የሚል ይጨምራል፣ መዝ. 81:3 ላይ፣ ይኸውም የዳስ በዓል ወር የሆነ።

ሐ. ይህ መዝሙር በግልጽ የሚጠቅሰው ዘጸአትን እና የምድረ-በዳውን ሁኔታ ነው፣ ስለዚህ ሁለቱም ፋሲካና የዳስ በዓል ይስማማቸዋል። እኔ የሚመስለኝ የዳስ በዓል ወይም የማደሪያው ድንኳን ነው፣ ይኸውም የምድረ-በዳው እንክርት የሚታሰብበት። ጀፒኤስኦኤ የሚለው እሱ የሚያመለክተው "የአዲስ ዘመን" የአምልኮ ውዳሴ ነው። አስቸጋሪ የሚሆነው፣ መዝ. 81፡4 ሁለት የተለያዩ ቀናትን የሚጠቅስ መምሰሉ ነው (ማለትም፣ የወሩ መጀመሪያ እና የወሩ እኩሌታ)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 81፡1-5**

[1]በረድኤታችን በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ፥
ለያዕቆብም አምላክ እልል በሉ።
[2]ዝማሬውን አንሡ ከበሮንም ስጡ፥
ደስ የሚያሰኘውን በገና ከመሰንቆ ጋር
[3]በመባቻ ቀን በከፍተኛው በዓላችን ቀን
መለከትን ንፉ
[4]ለእስራኤል ሥርዓቱ ነውና፥
የያዕቆብም አምላክ ፍርድ።
[5]ከግብጽ በወጣ ጊዜ
ለዮሴፍ ምስክር አቆመው።
ያላወቅሁትን ቋንቋ ሰማሁ።

**81፡1-5** ይህ አንጓ የመዝሙረኛው ማሳሰቢያ ነው፣ ለኪዳኑ ሕዝብ፣ በያህዌ ብርቱ ማዳን እንዲደሰቱ፣ እስራኤልን ከግብፅ ባርነት ያወጣበትን።

1. በደስታ ዘምሩ – ቢ.ዲ.ቢ. 943፣ ኬቢ. 1247፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 32:11
2. በደስታ እልል በሉ – ቢ.ዲ.ቢ. 929፣ ኬቢ. 1206፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
3. ዝማሬውን አንሡ – ቢ.ዲ.ቢ. 669፣ ኬቢ. 724፣ *ቃል ተተኳሪ*
4. ከበሮንም ስጡ – ቢ.ዲ.ቢ. 678፣ ኬቢ. 733፣ *ቃል ተተኳሪ*
5. መለከትን ንፉ – ቢ.ዲ.ቢ. 1075፣ ኬቢ. 1785፣ *ቃል ተተኳሪ*

የቃላት መቀያየሩን ተመልከቱ በቁ. 1 እና 2፤ ቁ. 3 እና 4 መካከል ያለውን።

**81፡1 "ለእግዚአብሔር ለብርታታችን"** "ብርታት" (ቢ.ዲ.ቢ. 738) ዘወትር የሚያያዘው ከ "ረድኤት" ጋር ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መታመኛ) እግዚአብሔርን ለመግለጽ (መዝ. 14:6፤ 46:1፤ 62:6-7)። የታማኝ ተከታዮች ተስፋ፣ ሰላም፣ እና ደስታ በእርሱ ነው ያለው፣

1. በግል ጥረት
2. በሁኔታዎች
3. በሥጋዊ ሀብት ሳይሆን

**81፡3 "ከበሮ"** ይህ የሙዚቃ መሣርያ (ቢ.ዲ.ቢ. 1074) አነስተኛ በእጅ የሚያዝ፣ ክብ ነገር ሆኖ የእንስሳት ቆዳ የተወጠረበት ነው። እርሱም ከሴቶች ዳንስ ጋር ይያያዛል በዘጸአት ድል ላይ፣ ዘጸ. 15፡20 ላይ (ደግሞም መሳ. 11፡34፤ 1 ሳሙ. 18፡6 ተመልከት)።

**81፡3** ይህ ቁጥር ማስጠንቀቂያ ነው፣ እግዚአብሔርን በተገቢ ጊዜና ስፍራ ማምለክ እንደሚገባ።

1. በአዲስ ጨረቃ (በመባቻ ቀን) — አዲስ ጨረቃን (መባቻን) ለማመልከት የእስራኤል መንገድ (ቢ.ዲ.ቢ. 294፣ ማለትም፣ ሙሉ ለሙሉ ጨለማ ዘኍ. 10:10፤ 28:11-15)
2. ሙሉ ጨረቃ (ቢ.ዲ.ቢ. 409፣ ማለትም፣ ሙሉ ለሙሉ ብርሃን፣ የእርሱ አጠቃቀም እዚህጋ እና ምሳ. 7፡20 ላይ ነው የሚገኘው፤ እሱም የወሩን እኩሌታ ያመለክታል)
3. የበዓል ቀን (የበርካታ በዓል ቀናት ዝርዝር፣ ዘጸአት 23 እና ሌዋውያን 23)

በሚያስገርም መልኩ ሰንበታት አልተጠቀሱም (1 ዜና. 23:31፤ 2 ዜና. 2:4፤ ሆሴ. 2:11)።

**ልዩ ርዕስ፡ የጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ የቀን መቁጠሪያዎች (ካሌንደር)**

▣ **"መለከትን ንፉ"** ይህ መሣርያ (ቢ.ዲ.ቢ. 1051) ዘጸ. 19፡16፣19 ላይ ተጠቅሷል፣ እስራኤል ራሷን ስታዘጋጅ፣ ያህዌ ሕጉን ሊሰጣት ሲል። ይህም እንደገና የዘጸአት ልምድ ጠቃሽ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ በእስራኤል ጥቅም ላይ የዋሉ ቀንደ መለከቶች።

ልዩ ርዕስ፡ የእስራኤል በዓላት

**81፡4-5 "ፍርድ... ሥርዓት... ምስክር"** እነዚህ ቃላት ያህዌ ለእስራኤል ያደረገውን መገለጦች ማሳያ መንገዶች ናቸው።

1. ፍርድ – ቢ.ዲ.ቢ. 349
2. ሥርዓት – ቢ.ዲ.ቢ. 1048
3. ምስክርነት – ቢ.ዲ.ቢ. 730

በዐውደ-ጽሑፍ እነዚህ የሚያመለክቱት ስለ በዓል ቀናት መገለጦች ነው (ዘጸአት 23፤ ሌዋውያን 23)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ።

እነዚህ ሕግጋት መዝ. 81፡5ሐ ምን እንደሆነ ዋነኛ ነጥቡን የሚያሳዩ ናቸው።

1. የዮሴፍ ምስክርነት በያህዌ ላይ ባለው እምነት በግብፅ ውስጥ በተጓዘበት መንገድ
2. የሙሴ ምስክርነት ከያህዌ ስለ መቅሠፍቶቹ ትንቢቱን እንደተከፋፈለ
3. የግብፃውያን ቋንቋ፣ እሱም ዕብራውያን በመጀመሪያ ያልተረዱት
4. የያህዌ ሕግጋት፣ እስራኤል የተወወ (መዝ. 81:8፣11፣13)
5. አስፈሪው የአምላክ ድምጽ፣ በሲና ተራራ (ማለትም፣ መዝ. 81:5ሐን ከመዝ. 81:6 ጋር ያዛምዳል) በዕብራይስጥ የተነገረ፣ በዚህን ጊዜም አብዛኞቹ እስራኤላውያን ሊረዱት አልቻሉም፣ ምክንያቱም ግብፅኛን ስለሚናገሩ። እንደዚያ ከሆነ፣ መዝ. 81፡5ሐ ባመዛኙ አንደኛ መደብ ተባዕታይ ነጠላ ግሥ ነው፣ እሱም ያህዌን የሚገልጽ።

**81:5** “ያልታወቀ ቋንቋ” ይህ በጥሬው ፈሊጥ ነው፣ እስራኤል በግብፅ በነበረበት ጊዜ (መዝ. 114:1)። እሱም ደግሞ ለከነአን መወረርና መያዝ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል

1. በሶርያ — ዘዳ. 28:49
2. በባቢሎን — ኤር. 5:15

አብዛኞቹ ዘመናዊ ትርጉሞች መዝ. 81:5ሐን የሚመለከቱት ከ81:6 ጋር እንደሚሄድ ነው፣ ከ 81:5ለ ጋር ሳይሆን። እንደዛ ከሆነ፣ እሱ የሚያመለክተው ያህዌ በሲና ተራራ ላይ እንደሚናገር ነው (ማለትም፣ በዕብራይስጥ ወይም በነጎድጓድ)። እስራኤል ፈርቶ ነበር የያህዌን ኃይለኛ አካላዊ መገለጥ፣ በሲና ተራራ ላይ (ዘጸአት 19-20)።

ቀሪዎቹ ቁጥሮች ያህዌ ሲናገር ነው የተመዘገቡት (ማለትም፣ መዝ. 81:6-16)።

---

***መዝሙር : 81:6-10***

**6ጫንቃውን ከሸክም፥**
**እጆቹንም በቅርጫት ከመገዛት አራቅሁ።**
**7በመከራህ ጊዜ ጠራኸኝ አዳንሁህም፥**
**በተሰወረ ዐውሎም መለስሁልህ፥**
**በክርክር ውኃ ዘንድም ፈተንሁህ። ሴላህ**
**8ሕዝቤ ሆይ፥ስማኝ እነግርሃለሁም**
**እስራኤል ሆይ፥ እመሰክርልሃለሁ።**
**9አንተስ ብትሰማኝ ሌላ አምላክ አይሆንልህም፥**
**ለሌላ አምላክም አትሰግድም።**
**10ከግብጽ ምድር ያወጣሁህ**
**እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝና**
**አፍህን አስፋ እሞላዋለሁም።**

---

**81:6-10** ይህ አንጓ የያህዌ ግርማዊ ድርጊቶች ማጠቃለያ ነው፣ በዘጸአትና በምድረ-በዳ መንከራተት ዘመን። ሁሉንም አንደኛ መደብ ተባዕታይ ነጠላ ግሦች ተገንዘብ! ያህዌ በቀጥታ ነው ለሕዝቡ የሚናገረው።

1. አቃልያለሁ (“አስወግጃለሁ”)፣ መዝ. 81:6 – ቢዲቢ 693፣ ኬቢ 747፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ
2. አድኛለሁ (“ማዳን”)፣ መዝ. 81:7 – ቢዲቢ 322፣ ኬቢ 321፣ *ፒል* ያልተጠናቀቀ ከ*ዋው* ጋር
3. መልሼአለሁ፣ መዝ. 81:7 – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
4. ፈተንሁህ፣ መዝ. 81:7 – ቢዲቢ 103፣ ኬቢ 119፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
5. እመሰክርልሃለሁ፣ መዝ. 81:8 – ቢዲቢ 729፣ ኬቢ 795፣ *ሂፊል* ተጓዳኝ
6. እኔ እግዚአብሔር አምላክህ ነኝና፣ መዝ. 81:10 – የኪዳን ቋንቋ
7. እሞላዋለሁ፣ መዝ. 81:10 – ቢዲቢ 569፣ ኬቢ 583፣ *ፒል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

ደግሞም ተገንዘብ

8. አሳልፌ ሰጠኋቸው፣ መዝ. 81:12 – ቢዲቢ 1018፣ ኬቢ 1511፣ *ፒል* ያልተጠናቀቀ ከዋው ጋር (ሮሜ. 1:24፤26፤28)
9. እኔ ፈጥኜ አሸንፋለሁ፣ መዝ. 81:14
10. እመግብሃለሁ፣ መዝ. 81:16 – ቢዲቢ 37፣ ኬቢ 46፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ ከዋው ጋር
11. አጠግብሃለሁ፣ መዝ. 81:16 – ቢዲቢ 959፣ ኬቢ 1302፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ

ያህዌ ይናገራል ከመዝ. 81:6 እስከ 16 በካህን ወይም በነቢይ በኩል።

**81:6** ይህ ቁጥር የሚያመለክተው የዕብራውያን ባሮች የግዳጅ ሥራ ነው (ማለትም፣ ዘጸ. 1:8-14)።

**81:7 “በመከራህ ጊዜ ጠራኸኝ አዳንሁህም፥”** ይህ የያህዌና የሙሴ ንግግር ጠቃሽ ነው፣ ዘጸ. 3:7-10።

▣ **“በተሰወረ ዐውሎም መለስሁልህ፥”** ይህ የሚጠቅሰው የእስራኤልን የሲና ተራራ ልምምድ ነው (ዘጸ. 19:19፤ 20:18)።

▣ **“በመሪባ በክርክር ውኃ ዘንድም ፈተንሁህ”** ይህ የሚያመለክተው የእስራኤልን ልምምድ ነው፣ ዘጸ. 17:6-7 እና ዘኁ. 20:13 ላይ የተመዘገበ። ኤቢ (ገጽ. 265-266) ይሄንን ስንኝ የሚመለከተው “ምንም እንኳ ባንተ ብተነኮስም” በሚል ነው (ዘጸ. 17:7፤ ዘኁ. 14:22፤ 20:24፤ 27:14፤ ዘዳ. 33:8፤ መዝ. 93:8-9)። እነዚህ እያንዳንዳቸው ጽሑፎች የሚያስቀምጡት እስራኤል እግዚአብሔርን እንደፈተነ ነው፣ እግዚአብሔር እስራኤልን መፈተኑን ሳይሆን።

ዘዳግም 33:8 የሚደግፍ የሚመስለው የኤምቲን መዝ. 81:7ሐ ነው፣ እግዚአብሔር እስራኤልን እንደፈተነ።

**“ሴላህ”** ማስታወሻ ተመልከት መዝሙር 3:2 ላይ።

**81:8 “ስማ”** ይህ *ቃል* ተተኳሪ ነው! እሱም የሚጀምረው ተከታታይ በሆኑ ማጣቀሻዎች ነው፣ ለእስራኤል ተገቢ ምላሽ አለመስጠት፣ ለያህዌ መገለጥ (ነህ. 9:34)።

1. ብትሰማኝ ኖሮ – መዝ. 81:8
2. ሕዝቤ አልሰማኝም – መዝ. 81:11
3. እስራኤል አልታዘዘኝም — መዝ. 81:11

4. ሕዝቤስ ሰምቶኝ ቢሆን — መዝ. 81፡13

ዴሪክ ኪድነር በቲንዳሌ ሐተታ ተከታታይ ላይ (ገጽ 326)፣ የሚለው “ሕዝቤ ሆይ ስማኝ” ነው፣ የሼማ ጸሎትን የዘዳ. 6፡4-6ን በመጥቀስ። በርግጥ ሊሆን ይችላል!

**81፡9** እስራኤል ታዞ ነበር፣ የባዕድ ጣዖቶችን እንዳይሠራ ወይም ተከትሎ እንዳይሄድ (ዘጸ. 20፡3፣23)። እስራኤላውያን በከነአን የመራባት ጣዖት ተማርከው ነበር። የእስራኤል የተለየነት በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አሀዳዊ አምልኮቷ ነበር፣ ይኸውም ምንም ተገዳዳሪ የማይፈቅድ!

የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 1374) የሚያስረግጠው መዝ. 81፡9-10 የዘጸ. 20፡1-2፤ ዘዳ. 5፡6 ጠቃሽ እንደሆነ ነው፣ ነገር ግን በተገላቢጦሽ ቅደም ተከተል (ተራ)።

**81፡10** ይህ የሚያመለክተው የያህዌን ምግብና ውኃ ሰጭነት ነው በምድረ-በዳ መንከራተት ዘመን።

## መዝሙር ፡ 81፡11-16

**11ሕዝቤ ግን ቃሌን አልሰሙኝም፥**
**እስራኤልም አላዳመጠኝም።**
**12እንደ ልባቸው *ሥራ* ተውኋቸው፥**
**በልባቸውም አሳብ ሄዱ።**
**13ሕዝቤስ ሰምቶኝ ቢሆን፥**
**እስራኤልም በመንገዴ ሄደው ቢሆን**
**14ጠላቶቻቸውን ፈጥኜ ባዋረድኋቸው ነበር፥**
**በሚያስጨንቋቸውም ላይ እጄን በጣልሁ ነበር**
**15የእግዚአብሔር ጠላቶችም በተገዙለት ነበር፥**
**ዘመናቸውም ለዘላለም በሆነ ነበር**
**16ከስንዴም ስብ ባበላቸው ነበር፥**
**ከዓለቱም ማር ባጠገባቸው ነበር።**

**81፡11-16** ይህ አንጻ በተቃርኖ ያስቀምጣል፣ እስራኤል ያደረገውን፣ ያህዌ ለእነርሱ ሊያደርግ ከሚፈልገው አኳያ።

1. የእስራኤል የዓመጻ ታሪክ (መዝ. 78:17፣40)
   ሀ. አልሰማም
   ለ. አልታዘዘም
   ሐ. አስቸጋሪ ልብ አለው
   መ. በገዛ ራሳቸው ሐሳብ ሄዱ
2. የያህዌ ምላሽ
   ሀ. ፍርድ
      (1) አሳልፎ ሰጣቸው (መዝ. 78:29፤ ኢሳ. 6:9-10፤ ሮሜ. 1:24፣26፣28) ለልባቸው *ሥራ*፣ መዝ. 81፡12
      (2) አሳልፎ ሰጣቸው፣ በራሳቸው ሐሳብ እንዲሄዱ፣ መዝ. 81፡12
      (3) ትእዛዝን በማያከብሩ ላይ የዘላለም ጥፋት *ሥ*ቃይ አለ፣ መዝ. 81፡15
   ለ. የእርሱ ሐሳብ
      (1) እሱን ይሰሙት ዘንድ፣ መዝ. 81፡13
      (2) በእርሱ መንገድ ይሄዱ ዘንድ፣ መዝ. 81፡13
   ሐ. የእርሱ ባርኮቶች
      (1) ጠላቶቻቸውን ያዋርዳቸዋል፣ መዝ. 81፡14
      (2) እጆቹን በጠላቶቻቸው ላይ ያዞራል፣ መዝ. 81፡14
      (3) ይመግባቸዋል
         (ሀ) ምርጥ የሆነውን ስንዴ (ዘዳ. 32፡14)
         (ለ) የዓለቱን ማር (ማለትም፣ የምድሪቱ ምርጥ ምግብ፣ ዘዳ. 32፡13)
      (4) ያጠግባቸዋል

# መዝሙር 82
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእቅ** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ፍትሐዊ ያልሆነ ፍርድ ተገሥጸ<br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>የአሳፍ መዝሙር | ስለ ፍትሕ ጸሎት | የጌታ ፍርድ ሥርዓት በጣዖት አማልክት | እግዚአብሔር ሉዓላዊው ኀኘር | ተቃርኖ በአሕዛብ ፈራጅ ላይ |
| 82:1-4 | 82:1-4 | 82:1-4 | 82:1-4 | 82:1 |
| | | | | 82:2-3 |
| | | | | 82:4 |
| 82:5-8 | 82:5 | 82:5 | 82:5-7 | 82:5-7 |
| | 82:6-7 | 82:6-7 | | |
| | 82:8 | 82:8 | 82:8 | 82:8 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ሦስተኛው አንቀጽ*
4. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. የዚህ መዝሙር ርግጠኛው ጥያቄ "ለማነው የተጻፈው?" የሚል ነው።
1. ለእስራኤላዊ ፈራጆች (*ኤሎሂም* ጥቅም ላይ የሚውለው ለእስራኤላዊ ፈራጆች ነው፣ ዘጸ. 21:6፤ 22:8-9፤ ደግሞም ታርጒምን እና በተለይም መዝ. 58፡1)
2. ጣዖታዊ ፈራጆች (አየተመቅ እና አኢመቅ ምንባቦች መዝ. 81:8 ላይ ተጠቅሰዋል) ወይም ጣዖት አምላኪ ነገሥታት (አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 825)
3. የጣዖት አማልክት (አእት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 953፤ ኤቢ፣ ገጽ. 268፣ ሕዝ. 28:1-10 በመጠቀም፣ እንደ ትይዩ፤ እና ኒዶቲ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 216)
4. ብሔራዊ አለቆች (ዘዳ. 4:19፤ 32:8፣ የአሕዛብ አለቆች፣ ዳን. 10:13)
5. የሰማያዊው ጉባኤ መላእክት (ማለትም፣ "*የኤሎሂም* ልጆች፣ መዝ. 8:5፤ 95:3፤ 96:4፤ 97:7፤ 138:1፤ ኢዮብ 1:6፤ 38:7

ለ. የኤሎሂም ፍርዶች (ማለትም፣ አንዱ) ከኢሎሂም ፍርዶች ጋር ይቃረናል (ማለትም፣ ፈራጆች ወይም መላእክት)። መዝሙር 82፡7 መላእክትን ያሳያል!

ሐ. ኢየሱስ ይሄንን መዝሙር ተጠቅሟል፣ ዮሐንስ 10፡31-38 ላይ፣ እዚያም እሱ የተመለከተው የሰው ፈራጆችን እንደሚጠቅስ ነው። እንደማስበው ኢየሱስ መዝሙር 82ን ጠቅሷል ነገር ግን አጠቃቀሱ ዘጸ. 21:6፤ 22:8-9ን ነው። የእሱ ነጥብ "ኤሎሂም" በበርካታ መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል እንደሚችል ነው!

የአአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ የሚያስረግጠው ኢየሱስ የሚታወቀውን ራቢያዊ ትርጒም የተጠቀመው በእርሱ ላይ የተነሣውን የተሳሳተ ክስ ለማሳየት ነው (ገጽ 825)።

መ. እሱም የሚመስለው የከነአን ጣዖት አምልኮ ምስያ፣ ይኸውም የመላእክትን ጉባኤ የሚያካትተው፣ የያህዌን ለማስረገጥ ጥቅም ላይ ውሏል
1. የሞራል ባሕርይ

2. ዩኒቨርሳል ገዥነት

ብኪ. አዘውትሮ የጥቅምን (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ምስያ ይጠቀማል፣ እውነትን ለማስተላለፍ፣ የጣዖት አምልኮ አፈ-ታሪክ እውነታ ሳያስረግጥ (ማለትም፣ [1] ሁከቱን አሸንፏል፣ የውኃውን አውሬ፣ [2] የሕይወት ዛፍ፤ [3] የበአልን ድርጊትና መጠሪያ፣ ወዘተ)። ምናባዊ ምስያ እውነታን ያስተላልፋል፣ የወደቀው የሰው ልጅ ማዕከላዊዎቹን እውነቶች ሊጨብጥ በሚችልበት መንገድ! ያህዌ እጅግ ታላቅ ነው፣ ሰዎች ሊገምቱት ከሚችሉት በላይ፣ ከእርሱ መለየትም እጅግ የከፋ ነው!

እሱም በርግጠኝነት ለማወቅ አስቸጋሪ ነው የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ምናባዊ ምስያ እና የመጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ዶክትሪናዊ እውነት ምን እንደሆነ። ምዕራባውያን በጥሬው መመልከት ላይ ሲያዘነብሉ መጽሐፍ ቅዱስ ደግሞ ሥነ-ጽሑፋዊ ጥራት አለው። ጥሬው ዘወትር በበቂ ሁኔታ ወይም በትክክል የዋናውን ደራሲ ሐሳብ ላያስተላልፍ ይችላል።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

> ***መዝሙር ፡ 82፡1-4***
>
> **[1]እግዚአብሔር በአማልክት ማኅበር ቆመ፥**
> **በአማልክትም መካከል ይፈርዳል።**
> **[2]እስከ መቼ ሐሰትን ትፈርዳላችሁ?**
> **እስከ መቼ ለኃጢአተኞች ፊት ታደላላችሁ? ሴላህ**
> **[3]ለድሆችና ለድሀ አደጎች ፍረዱ**
> **ለችግረኛውና ለምስኪኑ ጽድቅ አድርጉ**
> **[4]ብቸኛውንና ችግረኛውን አድኑ**
> **ከኃጢአተኞችም እጅ አስጥሉአቸው።**

**82፡1 "እግዚአብሔር"** ይህ *ኤሎሂም* የሚለው መጠሪያ ነው (ቢዲቢ 43፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች)። እሱም በዚህ ቁጥር ላይ ሁለት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እንዲሁም በድጋሚ መዝ. 82፡6 እና 8 ላይ።

አጠቃላዩ ቃል ኤል (ቢዲቢ 42) የመለኮት የተለመደ ስም ነው፣ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ)።

▣ **"አቋሙን ይይዛል"** እዚህ፣ ይህ ቃል (ቢዲቢ 662፣ ኬቢ 714፣ *ኒፋል አንቀጽ*) ጥቅም ላይ የዋለው ለኢሎሂም ነው (አንዱ፣ ነጠላ አንቀጽን በመጠቀም) ሥልጣናዊ አቋምን በመያዝ (ተመሳሳይ ቃል ጥቅም ላይ ውሏል "ሙሉ ለሙሉ መቆጣጠር" በሚል፣ 1 ሳሙ. 19:20 ላይ) በ"ኤል ማኅበረ-ምዕመናን ላይ።" ይህም ሰማያዊውን ጉባኤ ያመለክታል (1 ነገ. 22:19፤ 2 ዜና. 18:18፤ ኢዮብ 1:6፤ 2:1)፣ ሊሆን የሚችለውም

1. የሚያመልኩ መላእክት
2. ብሔረ መላእክት፣ ዘዳ. 32:8፤መዝ. 89:5-8፤ ኢሳ. 6:1፤ 24:19
3. አገልጋይ መላእክት፣ ኢዮብ 38:7፤ ዳን. 7:9-10

**82፡2-4** እነዚህ ቁጥሮች የያህዌን የተገለጠ ፍቃድ ይወክላሉ በፔንታቲዩች (ማለትም፣ ዘፍጥረት - ዘዳግም)። ተናጋሪው ያህዌ ነው፣ መዝ. 82፡2-4 ላይ።

1. ለኃጢአተኛ ወገንተኝነትን አታሳይ (ሌዋ. 19:15፤ ዘዳ. 1:17፤ 16:19፤ ይህም የሆነው ያህዌ ሳያዳላ ስለሚፈርድ ነው፣ ዘዳ. 10:17)
2. ደካማውን ደግፍ – ቢዲቢ 1047፣ ኬቢ 1622፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. ለድሀ-አደጉ ፍረዱለት (በተተኳሪ መልኩ ከቁ. 2፣ ዘዳ. 24:17)
4. ለተቸገረው ፍረዱ – ቢዲቢ 842፣ ኬቢ 1003፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
5. ለምስኪኑ ፍረዱለት – በተተኳሪ መልኩ ከቁ. 4
6. ደካማውን ታደጉ – ቢዲቢ 812፣ ኬቢ 930፣ *ፒል ተተኳሪ*
7. ችግረኛውን ታደጉ – በተተኳሪ መልኩ ከቁ. #6
8. ከኃጢአተኛ እጅ አድኗቸው (ከመዝ. 82:2ለ ጋር ወደ ኋላ ይያያዛል) – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

ሰብዓዊ ፈራጆች፣ የእስራኤል ፈራጆችም ቢሆኑ፣ ፍትሐዊ ባልሆነ መልኩ ይሠራሉ፣ በፍርዶቻቸው። ባጠቃላይ እነርሱ በመልአካዊ ዓመጻ እና በውድቀት ተጽዕኖ ሥር ናቸው። መዝሙር 82፡5-7 የሚያመለክተው ተገቢ ያልሆነ መልአካዊ ድርጊቶችን ነው፣ እንዲሁም የእግዚአብሔርን ፍርድ በእነርሱ ላይ (መዝ. 82፡7ሀ)።

**82፡2** ግልጽ የሆነ ተቃርኗዊ ቅንብር አለ በኤሎሂም (ማለትም፣ አንዱ እውነተኛው አምላክ) እና በብዙ ቁጥሩ ኤሎሂም (ማለትም፣ የመላእክት ጉባኤ) መካከል። ይህም የሚያመለክተው ብሔረ-መላእክትም ደግሞ ያህዌ ለእስራኤል ያደረገውን ኪዳናዊ መገለጦች ችላ እንዳሉ ነው፣ በተለይም አቅመ-ቢስና ችግረኛ የኅብረተሰብ ክፍሎችን። እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ይወዳል፣ በአምሳሉ የተፈጠሩትን፣ የሰው ልጆችን ሁሉ!

▣ **"አድልኦ ማሳየት"** ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) በጥሬው "ፊትን ማንሣት ነው።" እሱም ሰውን ለመገንዘብና ለመቀበል ማሳያ መንገድ ነው (ዘፍ. 32:20፤ ኢዮብ 42:8-9)። ሆኖም፣ ለዳኛ እሱ የሚሆነው ለአንዱ ሞገስ ማሳየትን ወይም አድሏዊነት ነው እናም ኩንን ነው (ዘዳ. 1:17፤ 16:19፤ ሌዋ. 19:15፤ ኢዮብ 13:8፤ 32:21፤ 34:19፤ ምሳ. 17:15፤ 18:5፤ 24:23፤ 28:21)።

▣ **"ሴላህ"** መዝሙር 3፡2 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

**መዝሙር ፡ 82፡5-8**

[5]አያውቁም፥ አያስተውሉም
በጨለማ ውስጥ ይመላለሳሉ
የምድር መሠረቶች ሁሉ ተናወጡ።
[6]እኔ ግን። አማልክት ናችሁ፥
ሁላችሁም የልዑል ልጆች ናችሁ
[7]ነገር ግን እንደ ሰው ትሞታላችሁ፥
ከአለቆችም እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ አልሁ።
[8]አቤቱ፥ ተነሥ፥ በምድር ላይ ፍረድ፥
አንተ አሕዛብን ሁሉ ትወርሳለህና።

**82፡5-8** ይህ አንጓ ሰዎችን የሚጠቅስ ሊሆን አይችልም፣ ነገር ግን መላእክትን የሚጠቅስ እንጂ።

1. "የምድር መሠረቶች ሁሉ ተናወጡ"
2. እናንተ አማልክት ናችሁ (ማለትም፣ ኤሎሂም)
3. የልዑል ልጆች (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር ልጆች [ዘፍጥረት 6])
4. እንደ ሰዎች ትሞታላችሁ
5. ከአለቆችም እንደ አንዱ ትወድቃላችሁ ("አለቆች" ለብሔረ መላእክት ጥቅም ላይ ውሏል፣ ዳን. 10፡5፣20 ላይ፤ ነገር ግን ሰዎች ኢሳ. 3፡13-14)
6. በምድር ላይ ይፈርዳሉ… አሕዛብን ሁሉ ይወርሳሉ

**82፡5** በመዝሙሩ ላይ የተመለከቱት ባሕርያቸው

1. አያውቁም
2. አያስተውሉም
3. በጨለማ ይመላለሳሉ

እነዚህ፣ እንደ መዝ. 82፡2-4፣ እስራኤላውያንን ሊያመለክቱ ይችላሉ። በዚህ ምክንያት ነው አንዳንድ ኢታቾች "ኤሎሂም"ን የሚወስዱት፣ መዝ. 82፡1ለ እና 6ሀ ላይ፣ የሰው አለቆችን እንደሚጠቅስ (ዘጸ. 21:6፤ 22:8-9)። እንደሚመስለኝ የመዝሙሩ አጠቃላይ ማስረጃ የሚያመለክተው ብሔረ መላእክትን ነው።

መዝ. 82፡2-4 ያህዌ ሲናገር የሚያሳይ ከሆነ፣ መዝ. 82፡5-7 ማነው የሚናገረው? መዝሙረኛው ራሱ መሆን አለበት፣ እንደ መዝ. 82፡6፣ 7፣ እና 8 የመጀመሪያ ቃላት አኳያ፣ ባጠቃላይ፣ የሚጠይቅ ይመስላል። ሆኖም፣ የግድ መቀበል የሚገባው፣ እነርሱ ደግሞ የያህዌን የራሱን ቃላት ሊያንጸባርቁ ይችላሉ (ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ 730)።

▣ **"በጨለማ ውስጥ ይመላለሳሉ"** "መመላለስ" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ *ሂዝፓል ያልተጠናቀቀ*) የሕይወት ስልት ድርጊትን ይገልጻል።

"ጨለማ" የክፉ ወይም የእግዚአብሔርን ራዕይ መናቅ ዘይቤ ነው። ጽንሰ-ሐሳቡ በበርካታ ፈሊጦች ይገለጻል።

1. የጨለማ መንገዶች – ምሳ. 2:13፤ 4:19፤ ኢሳ. 9:2፤ 50:10፤ ዮሐንስ 3:19-20
2. የጨለማ ሥራዎች – ኢዮብ 24:13-17፤ ኤር. 23:12
3. በጨለማ መመላለስ – ዘዳ. 28:29፤ ኢዮብ 5:14፤ 12:25፤ ኢሳ. 59:9-10
4. ብርሃኑን ጨለማ ማለት – ኢዮብ 17:12፤ ኢሳ. 5:20

መንፈሳዊ የሆነ ተብሎ ዕውርነት አስፈሪ ነገር ነው። ሁለቱም መላእክትና ሰዎች ሆን ብለው አለማየትን ይመርጣሉ (ኢሳ. 24:21)! እነርሱ የገዛ ራሳቸውን መንፈሳዊ ዓይኖች ያጠፋሉ!

▣ **"የምድር መሠረቶች ሁሉ ተናወጡ"** ይህ በሁለት መልክ ሊወሰድ ይችላል።

1. የሞራል መሠረቶች፣ መዝ. 11:3፤ ኢሳ. 24:7-13፣ በተለይ መዝ. 82:18
2. ሥጋዊ መሠረቶች፣ መዝ. 93:1፤ 96:10፤ 104:5

**82፡6 "የልዑል ልጆች"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር ልጆች፣ እዚያም ሐረጉን ዘፍጥረት 6 ላይ ያብራራሁበት። እዚያም ደግሞ መላእክትን የሚጠቅስ ይመስለኛል።

"ለልዑሉ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

**82፡7 "መውደቅ"** ኤቢ እንደሚያስረግጠው፣ ይህ የሚያመለክተው ወደ ሲኦል መውደቅን ነው፣ እናም ኢሳ. 14:12-15 እና ሕዝ. 28:1-10 እንደ ምሳሌ ይጠቀሙበታል (ገጽ 270)። እንደገናም፣ በመልአክ (ማለትም፣ ሰይጣን) እና በሰው (ማለትም፣ የባቢሎን ንጉሥ እና የጢሮስ ንጉሥ) መካከል ያለውን ውኅኅብር ተገንዘብ። እዚህጋ ምሥጢር አለ! ብኪ ምናባዊ ምስያን፣ ማነጻጸሪያን፣ እና ፈሊጦችን ይጠቀማል፣ ዘመናዊዎቹ ሙሉ ለሙሉ ሊረዱ በማይችሉበት መንገድ። በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) በመንፈሳዊ ዓለም እና በሥጋዊ ዓለም መካከል ክፍፍል የለም።

**82፡8** እነዚህ የመጨረሻ ሁለት ቃል ተተኳሪዎች ("ተነሥ" እና "ፍረድ") ሁለንተናዊ (ዩኒቨርሳል) አትኩሮት አላቸው። እግዚአብሔር ፈጣሪ ብቻ አይደለም ግን ደግሞ ዳኛም እንጂ ነው። እሱ በፍጥረት ሁሉ ላይ ይገዛል (መዝ. 2:8፤ ራዕ. 11:15)።

ኢየሱስ በፍጥረት ላይ ከያህዌ ጋር እንደሠራ (ዮሐንስ 1:3፣10፤ ሮሜ. 11:36፤ 1 ቆሮ. 8:6፤ ቆላ. 1:16፤ ዕብ. 1:2)፣ እሱ ደግሞ በፍርድ ላይ ከያህዌ ጋር ይሠራል (ዮሐንስ 5:22-23፣27፤ 9:39፤ ሐዋ. 10:42፤ 17:31፤ 2 ጢሞ. 4:1፤ 1 ጴጥ. 4:5)።

የመጨረሻው ቃል፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ ነው *ቃል* ተተኳሪ ሳይሆን። እሱም የሚያስረግጠው ያህዌ መግዛቱን ነው፣ እንደሚገዛ ሳይሆን። እሱም የእውነት ቃል ነው!

መልአካዊው ትርጉም እውነት ከሆነ (እናም መጠነኛ ጥርጣሬ አለ፣ ከኢየሱስ የዮሐንስ 10 አጠቃቀም የተነሣ)፣ እንግዲያውስ መዝሙረኛው እየጸለየ ነው፣ ያህዌ የጣዖት አማልክትን ወይም ብሔረ መላእክትን እንዲያሸንፍ፣ ብሎም የጽድቅ ሥርዓቱን በምድር ሁሉ ላይ እንዲያሰፍን፣ በመጀመሪያ በዔድን እንዳደረገው (ከውድቀት፣ ከጥፋት ውኃ፣ እና/ወይም ከባብኤል ግንብ በፊት)። አንድ ቀን እንደዚያ ይሆናል (1 ቆሮንቶስ 15፡24-28)!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የሰማያዊውን ጉባኤ ጽንሰ-ሐሳብ አብራራ። እሱስ የተቋቋመው ከጻድቃን ወይስ ከክፉ መላእክት ነውን?
2. “የኤሎሂምን” ሁለት የተለያዩ አጠቃቀሞች አብራራ።
3. የዚህን መዝሙር ይዘቶች ማለትም ስለ “ሰዎች” የሚያመለክቱትን እና ስለ “መላእክት” የሚያመለክቱትን ዘርዝር።
4. ምን ማለታችን ነው፣ እግዚአብሔር የሞራልን ዩኒቨርስ ፈጥሯል ስንል?
5. መዝሙረኛውና ኢየሱስ መዝ. 82፡6ን በተመሳሳይ መንገድ ይጠቀሙበታልን?
6. “አለቆች” እነማናቸው፣ መዝ. 82፡7?
7. የመዝ. 82፡8 ዩኒቨርሳላዊ ግፊት ከቀሪው የመዝሙሩ ክፍል ጋር እንዴት እንደሚሰማማ አብራራ።
8. ቅዱስ ቃሉ የጥቅምን (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ምስያንና አፈ-ታሪክን ይጠቀማልን?

# መዝሙር 83
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር ጠላቶቹን እንዲያደነገግር ልመና <u>ኤምቲ መግቢያ</u> የአሳፍ መዝሙር | በእስራኤል ላይ የሚደረግ ሤራ እንዲከሽፍ ጸሎት | ጸሎት ከብሔራዊ ጠላቶች ለመታደግ | ጸሎት ለእስራኤል ጠላቶች ሽንፈት | በእስራኤል ጠላቶች ላይ |
| 83:1-8 | 83:1-4 | 83:1-8 | 83:1-4 | 83:1-2 |
| | | | | 83:3-4 |
| | 83:5-8 | | 83:5-8 | 83:5-8 |
| 83:9-12 | 83:9-12 | 83:9-12 | 83:9-12 | 83:9-12 |
| 83:13-18 | 83:13-18 | 83:13-18 | 83:13-18 | 83:13-18 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. የህዌ ከኪዳን ሕዝቡ ጋር የቅርብ ወዳጅነት አለው። የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አካባቢ ሕዝቦች እስራኤልን ለማጥቃት ማቀዳቸውና ማሴራቸው፣ እሱን ለማጥቃት እንደማሴር ነው (መዝ. 83:5 እና መዝ. 83:12 ላይ ያለ ማስታወሻ)።

ለ. በርካታ ሕዝቦችና የሕዝብ ወገኖች ተጠቅሰዋል።
1. ኤዶም
2. እስማኤላውያን
3. ሞአብ
4. አጋራውያን
5. ጌባል
6. አሞን
7. አማሌቅ
8. ፍልስጥኤም
9. ጢሮስ (ማለትም፣ ፍንቄ)
10. አሦር
11. ምድያም (ዘኁልቍ 11-14 የሚጠቅሰው የእስራኤልን ያለፈ ሁነት ነው፣ ያህዌ በረዳቸው ጊዜ)
12. ሲሳራ እና ጃቢን
13. ኦሬብ እና ዜብ
14. ኤባህ እና ስልማና

ሐ. ይህ የጸሎት መዝሙር (5 ተተኳሪዎች) ለእስራኤል ጠላቶች ጥፋት፣ ባሕርይ ያደረገው በበርካታ ቁጥር ተተኳሪዎች ነው፣ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ በዋሉ።
1. መዝ. 83:1 — ሁለት ተመልክተዋል ግን ሦስት ጥቅም ላይ ውለዋል
2. መዝ. 83:15-18 – ስድስት (ስምንት ሊሆኑ ይችላሉ፣ ከመዝ. 83:15 ጋር)

መ. ይህ መዝሙር በርካታ ስሞችን ለመለኮት ይጠቀማል።
1. እግዚአብሔር፣ መዝ. 83:1ሀ፣ 12ለ – *ኤሎሂም* (ቢዲቢ 43)
2. እግዚአብሔር፣ መዝ. 83:16 – *ኤል* (ቢዲቢ 42)
3. እግዚአብሔር መዝ. 83:13ሀ – *ኤሎአህ* (ቢዲቢ 43)
4. ጌታ፣ መዝ. 83:16ለ፣ 18ሀ – *ያህዌ* (ቢዲቢ 217)
5. ልዑሉ፣ መዝ. 83:18ለ – *ኤሊኦን* (ቢዲቢ 751)

ልዩ ርዕስ ተመልከት: የመለኮት ስሞች

ሠ. ይህ መዝሙር ጥንካሬ አለው
1. ወንጌላዊ ግፊት (ማለትም፣ መዝ. 83:16ለ፣ 18)
2. ዩኒቨርሳላዊ ትኩረት (መዝ. 83:18ለ)

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 83፡1-8**

**[1]አቤቱ፥ እንደ አንተ ማን ነው?**
**አቤቱ፥ ዝም አትበል፥ ቸልም አትበል።**
**[2]እነሆ፥ ጠላቶችህ ጮኸዋልና፥**
**የሚጠሉህም ራሳቸውን አንሥተዋልና።**
**[3]ሕዝብህን በምክር ሸነገሉአቸው፥**
**በቅዱሳንህም ላይ ተማከሩ።**
**[4]ኑ ከሕዝብ እናጥፋቸው፥**
**ደግሞም የእስራኤል ስም አይታሰብ አሉ።**
**[5]አንድ ሆነው በአንተ ላይ ተማከሩ**
**በአንተ ላይ ቃል ኪዳን አደረጉ**
**[6]የኤዶማውያን ድንኳኖች እስማኤላውያንም፥**
**ሞዓብም አጋራውያንም፥**
**[7]ጌባል አሞንም አማሌቅም፥**
**ፍልስጥኤማውያንም ከጢሮስ ሰዎች ጋር**
**[8]አሦርም ከእነርሱ ጋር ተባበረ፥**
**ለሎጥ ልጆችም ረዳት ሆኑአቸው። ሴላህ**

**83፡1-8** ይህ አንጓ የሚገልጸው የአካባቢውን ሕዝቦች ተገቢ ያልሆነ ድርጊት ነው። መዝሙረኛው ይጠይቃል፣ እግዚአብሔር በእስራኤል አኳያ ያደርግ ዘንድ።
1. ዝም አትበል – ቢዲቢ 198፣ ምንም ግሥ የለውም ግን ከቁ. 2፣ ቁ. 3 ጋር ትይዩ ነው
2. ጸጥ አትበል– ቢዲቢ 361፣ ኬቢ 357፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 28:1፤ 35:22፤ 50:3፤ 109:1
3. ቸልም አትበል (ማለትም፣ ንቁ ያልሆነ) – ቢዲቢ 1052፣ ኬቢ 1641፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

የአካባቢው ሕዝቦች ወረራቸውን ማቀዳቸውና መተግበራቸው (መዝ. 83:2-8) የኪዳኑን ሕዝቦች በያህዌ ዝም ማለት እንዲደነቁ አድርጓቸዋል።
የአካባቢውን ሕዝቦች ድርጊት ተገንዘብ።
1. ጮኸዋል – ቢዲቢ 242፣ ኬቢ 250፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 46:6 እንዲሁም እጅግ ተመሳሳይ ነው ከመዝ. 2:1-2 ጋር
2. ራሳቸውን ከፍ አድርገዋል (ራሳቸውን አንሥተዋል) – ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ መሳ. 8:28፤ ዘካ. 1:21
3. በተንኮል አቅደዋል – ቢዲቢ 791፣ ኬቢ 886፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ፣ እዚህጋ ብቻ በሂፊል፣ ብኪ ላይ
4. አንድ ላይ አሲረዋል – ቢዲቢ 419፣ ኬቢ 421፣ *ሂዝፔል* ያልተጠናቀቀ፣ "በጽኑ ቁርጠኝነት" ጥቅም ላይ የዋለ 2 ዜና. 30:23
   ሀ. ና – ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ *ቃል* ተተኳሪ
   ለ. ጥረጋቸው – ቢዲቢ 470፣ ኬቢ 469፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ መዝ. 74:8
   ሐ. ዳግመኛም የእስራኤል ስም እንዳይታሰብ – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ፣ እሱም ለአጠቃላይ ጥፋት እና ሞት ፈሊጥ የሆነ

የዚህ ዝርዝር ማጠቃለያ መዝ. 83:5 ላይ ተቀምጧል። እስራኤልን ማጥቃት ያህዌን ማጥቃት ነው፣ መዝ. 83:2፤ መዝ. 2:2፤ 74:18፣23።

**83:3 "ሕዝብህ. . . ያንተ የከበሩት"** ሁለተኛው ገለጻ (ቢዲቢ 860፣ ኬቢ 1049፣ *ቃል* ተገብሮ አንቀጽ) ሁለት ታሳቢ ፍችዎች አሉት በቢዲቢ።
1. መዝገብ (ጄፒኤስኦኤ)፣ ዘጸ. 19:5፤ ዘዳ. 7:6፤ 14:2፤ 26:18
2. ከእግዚአብሔር ጋር የተሸሸገ፣ መዝ. 27:5፤ 31:21

አኪጆት "የተጠጉት አንዱ" የሚል አለው (ቁ. 2)፣ አኢመቅ ግን "አንተ የምትንከባከባቸው" የሚል ሲኖረው (ቁ. 1)።

**83፡4ለ "የእስራኤል ስም"** ይህ ሕዝብን የመጥቀሻ መንገድ ነው (መዝ. 83፡4ሀ)።
"እስራኤል" ለሚለው ስም ፍቺ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እስራኤል (ስሙ)።

**83፡5 "ኪዳን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን።

**83:6 "ድንኳኖች..."** ይህ በሌላ ጊዜ የሆነ ፈሊጥ ነው፣ እስራኤል "በድንኳን" ውስጥ በሚኖርበት ጊዜ፣ ነገር ግን በዚህ ጊዜ አብዛኞቹ የሚኖሩት በከተሞችና በመንደሮች ውስጥ ነበር፣ በተሻሉ ቋሚ ቤቶች።

ሌለኛው አማራጭ እሱ ለሕዝብ ፈሊጣዊነቱ ነው (መዝ. 74:51፤ 120:5)።

ኤቢ (ገጽ 274) የጥቅል ብሄቂን ይጠቅሳል፣ በማሳዳ የተገኘውን፣ "የኤዶም አማልክት..." የሚል ያለው። ይህም በተሻለ ይሰማማል፣ "ክንድ" ከሚለው መዝ. 83፡8 ላይ ካለው ምስያ ጋር። እሱም ደግሞ በተሻለ ይያያዛል ከብሔረ መላእክት ጋር፣ ከመዝሙር 82። ኤቢ ይዘረዝራል ዪጋኤል ያርዲን፣ <u>የእስራኤል አሳሽ ጋዜጣ</u>፣ 15 (1965)፣ 104፣ ሐረጉን እንደ ማያ ስፍራ።

▣ **"ኤዶም"**

ልዩ ርዕስ፡ ኤዶምና እስራኤል

▣ **"እስማኤላውያን"** ይህ የሚያመለክተው የእስማኤልን ዝርዮች ነው፣ የአብርሃም የመጀመሪያ ልጅ ከአጋር (ዘፍ. 25፡12-16)። እነርሱ የዓረብ ነገድ ሆነዋል።

▣ **"ሞአብ"** ይህ ከሁለቱ ሕዝቦች አንደኛው ነው ከሎጥና ለሴቶች ልጆቹ ከተወለዱት (ዘፍ. 19:30-38፣ በተለይ መዝ. 83:37)።

▣ **"አጋራውያን"** ይህ ከእስማኤል የሆነ ነገድ ነው፣ 1 ዜና. 5:10፣18-22 ላይ ከተጠቀሰው። ስሙ ከ "አጋር" መጥቶ ሊሆን ይችላል፣ የእስማኤል ግብፃዊ እናት። እነርሱም ይኖሩ የነበሩት ከከነአን በስተምስራቅ ነበር፣ እናም አንዳንድ የነገዱ ክፍሎች እጅግ ወደ ደቡብ ምስራቅ ሲል።

**83፡7 "ጌባል"** ይህ ስም (ቢዲቢ 148፣ ኬቢ 174) ሁለት ታሳቢ ማጣቀሻዎች ሊኗሯቸው ይችላሉ።

1. "ተራራ" ከሚለው ቃል፣ ሊያመለክት የሚችለው የዮርዳኖስን ዳርቻ አካባቢ ነው፣ ከፔትራ አጠገብ፣ እዚያም ከዓረብ ነገድ ጋር የሚያያዝበት
2. ከፍንቂያውያን የድሮ የባሕር ዳርቻ ከተማ ስም አኳያ፣ እና ስለዚህ፣ ከጢሮስ ጋር ትይዩ ይሆናል (መዝ. 83፡7ለ)፣ ኋላ ላይም ባይብሎስ በመባል የሚታወቀው

▣ **"አሞን"** የሞአብን ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 83፡6 ላይ።

▣ **"አማሌቅ"** የኤሳው ዝርያ፣ እሱም የኤዶም አለቃ የነበረ (ዘፍ. 30:15-16)። እነርሱ በተለይ ለእስራኤል ችግር ፈጣሪ ነበሩ፣ በምድረ-በዳ የመንከራተት ዘመን (ዘጸ. 17:8-16፤ ዘኊ. 24:20፤ ዘዳ. 25:12-19። ሳኦል እነርሱን እንዲያጠፋ ታዞ ነበር (1 ሳሙኤል 15)።

▣ **"ፍልስጥኤም"** ፍልስጥኤማውያን ባጠቃላይ ግሪኮች ነበሩ ከኤጅያን ደሴቶች። እነርሱ ብቸኛ የሕዝብ ወገኖች ነበሩ፣ በዚህኛው የዓለም ክፍል የማይገረዙ። እነርሱ ባጠቃላይ ቅጥረኛ ኃይላት ነበሩ፣ በአስራ ሁለተኛው ክፍለ-ዘመን ቅ.ል.ክ ግብፅን ለማጥቃት ሙከራ ያደረጉ፣ ነገር ግን የተሸነፉ። ከዚያም በጥልስጥኤም ደቡባዊ ባሕር ዳርቻ ሰፈሩ። እነርሱም አምስት ዋነኛ ከተሞች ነበሯቸው፣ ኢያ. 13፡3 ላይ ድንበራቸው የተካለለ፡ ጋዛ፣ አሽዶድ፣ አስቀሎና፣ ጋድ፣ እና ኢክሮን። እነርሱም ዋነኞቹ ወታደራዊ ችግሮች ነበሩ፣ በመሳፍንት ዘመን ሁሉ፣ ብሎም በሳኦል እና በዳዊት አገዛዝ ዘመን ሁሉ። "ፍልስጥኤም" የሚለው ስም የመጣው "ፓልስታይን" ከሚለው ቃል ነው።

▣ **"ጢሮስ"** ይህ የታወቀ የባሕር ወደብ ነው፣ የፍንቄአዊያን ሰፊ ግዛት (ኢምፓየር)፣ ከእስራኤል በስተ ሰሜን። የድሮው ዋና ከተማ "ሲዶና" ነበር (እናም ከጌባል ጥንታዊ ሊሆን ይችላል)።

▣ **"አሦር"** ይህ ዋነኛው ሰፊ ግዛት (ኢምፓየር) ነበር፣ የጤግሮስ/ኤፍራጥስ። እሱም ኃይለኛ ነበር ከ900ዎቹ ቅ.ል.ክ እስከ 609 ቅ.ል.ክ መካከለኛ አካባቢ ድረስ፣ ዋና ከተማው ነነዌ ስትወድቅ (ናሆም)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የሜሶፖታሚያ ኃይላት ቅኝት (ጥናት) (አሦር፣ ባቢሎን፣ ፐርሺያ)።

የአሦር መጠቀስና የባቢሎን አለመጠቀስ ይህ መዝሙር መቼ እንደተጻፈ ቀኑን ፍንጭ የሚሰጥ ነው።

**83፡8** አሦራውያን ረዳት ሆነው ነበር ("ክንድ") ለዮርዳኖስ አካባቢ ሕዝቦች፣ እነርሱም የሎጥ እና የሁለት ልጆቹ ዝርያ የሆኑ (ዘፍ. 19፡30-38)።

1. ሞአብ
2. አሞን

▣ **"ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝሙር 3፡2 ላይ

***መዝሙር ፡ 83፡9-12***

**9እንደ ምድያምና እንደ ሲሣራ፥**
**በቂሶንም ወንዝ እንደ ኢያቢስ አድርግባቸው።**
**10በዓይንዶር ጠፉ፥**
**እንደ ምድርም ጉድፍ ሆኑ።**
**11አለቆቻቸውን እንደ ሔሬብና እንደ ዜብ፥**
**ታላላቆቻቸውንም እንደ ዛብሄልና እንደ ስልማና አድርጋቸው።**
**12የእግዚአብሔርን መሠዊያ**
**እንወርሳለን የሚሉትን።**

**83፡9-12** ይህ አንጓ ለዛን ጊዜዎቹ እስራኤላውያን ያስታውሳቸዋል፣ የያህዌን መገኘትና ዕርዳታ፣ ባለፉት ጊዜያት ወራሪዎች የእስራኤልን ምድር ለመውሰድ በሚያሴሩበት ጊዜ።

1. እንደ ምድያም — መሳ. 7፡22
2. ሲሣራ እና ኢያቢስ — መሳ. 4፡22-23
3. ሔሬብ እና ዜብ — መሳ. 7፡25
4. ዛብሄል እና ስልማና — መሳ. 8፡21

**83፡10 "እንደ ምድርም ጕድፍ"** ይህ የሚያመለክተው ከፍተኛ ቁጥር ያለው ሙት አካል ነው፣ ከጦርነት በኋላ። ያላግባብ የሆነ ቀብር ወይም በአራዊት መበላት የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ሰዎችን ያሸብራል (2 ነገ. 9:37፤ መዝ. 79:2-3፤ ኤር. 8:2፤ 22:19፤ 36:30)። ይህ የርግማን ማሳያ ነው!

▣ **"ዓይንዶር"** ይህ ስፍራ በሳኦል ጊዜ ተጠቅሷል፣ በመጽሐፈ መሳፍንት ላይ ሳይሆን። አእመቅ ዓይንሃሮድ በሚል ይቀይረዋል፣ እሱም መሳ. 7፡1 ላይ የተጠቀሰው፣ እናም ከመዝ. 83፡9-11 ጋር በታሪካዊ ጠቃሽነቱ የሚገጥም (ማለትም፣ መሳፍንት 4-8)። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 341) ለዓይንዶር "ሀ" ደረጃ ይሰጠውና ማስተካከያውን ይተወዋል። ምንም እንኳ በስም ባይጠቀስም፣ እርሱ ባጠቃላይ ስፍራው ላይ ይኖራል (ኢያ. 17፡ 11)።

## መዝሙር ፡ 83፡13-18

**13 አምላኬ ሆይ፥ እንደ ትቢያ**
**በነፋስ ፊትም እንደ ገለባ አድርጋቸው።**
**14 እሳት ዱርን እንደሚያቃጥል፥**
**ነበልባልም ተራሮች እንደሚያነድድ፥**
**15 እንዲሁ በቍጣህ አሳድዳቸው፥**
**በመቅሠፍትህም አስደንግጣቸው።**
**16 ፊታቸውን እፍረት ሙላው፥**
**አቤቱ፥ ስምህንም ይፈልጋሉ።**
**17 ይፈሩ ለዘላለሙም ይታወኩ**
**ይጐስቍሉ ይጥፉም።**
**18 ስምህም እግዚአብሔር እንደ ሆነ፥**
**በምድር ሁሉ ላይም አንተ ብቻ ልዑል እንደ ሆንህ ይወቁ።**

**83፡13-18** ይህ አንጓ ለያህዌ ጸሎት ነው፣ በፍርድ እንዲሠራ በእስራኤል በኩል።

1. አድርጋቸው – ቢዲቢ 1011፣ ኬቢ 1483፣ *ቃል ተተኳሪ*
   ሀ. እንደ ትቢያ በነፋስ ፊት እንደ ገለባ፣ ኢሳ. 17:13፤ 29:5፤ 41:15-16
   ለ. በነፋስ ፊት እንደ ገለባ፣ ኢሳ. 17:13
   ሐ. እሳት ዱርን እንደሚያቃጥል
   መ. ነበልባልም ተራሮችን እንደሚያነድድ
2. አሳድዳቸው – ቢዲቢ 922፣ ኬቢ 1191፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
3. አስደንግጣቸው – ቢዲቢ 96፣ ኬቢ 111፣ *ፒል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
4. ፊታቸውን እፍረት ሙላው – ቢዲቢ 569፣ ኬቢ 583፣ *ፒል ተተኳሪ*
5. ይፈሩ – ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
6. ይታወኩ – ቢዲቢ 96፣ ኬቢ 111፣ *ኒፋል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
7. ይጎስቁሉ – ቢዲቢ 344፣ ኬቢ 340፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
8. ይጥፉ – ቢዲቢ 1፣ ኬቢ 2፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*

ሌሎች ሁለት ተጨማሪዎች አሉ፣ የፍርድን ሁነኛ ዓላማ የሚያሳዩ፣ ይኸውም አሕዛብ ያህዌን ለማምለክ እንዲመጡ የሚረዱ (ልዩ ርዕስ ተመልከት: የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

1. ስምህን ይፈልጉ ዘንድ፣ አምላክ ሆይ – ቢዲቢ134፣ ኬቢ 152፣ *ፒል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ* (መዝ. 83:16)
2. በምድር ሁሉ ላይም አንተ ብቻ ልዑል እንደ ሆንህ ያውቁ ዘንድ – ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ* (መዝ. 83:17)

**83፡17** ትይዩውን ተገንዘብ በ "ዘላለም" እና "ሕያው" መካከል ያለውን። ይህም መዝ. 83፡4 ላይ ይንጸባረቃል፣ እዚያም አሕዛብ እስራኤል ሕልውናው እንዲያበቃ የሚፈልጉት!

**83፡18 "በምድር ሁሉ ላይ"** ይህ ዩኒቨርሳላዊ ይዘት በአሳፍ መዝሙር ላይ የተለመደ ነው! እሱም ግልጽ የሆነው የአሀዳዊነት አስፈላጊው መደምደሚያ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር የሚያንጸባርቀው በአሕዛብ ኅብረት ታሪካዊ ወረራ ነውን ወይስ ታሪካዊ ምናባዊ?
2. መዝ. 83፡1 የእስራኤልን ፍራቻና ውዥንብር እንዴት አድርጎ ሊያንጸባርቅ ይችላል?
3. መዝ. 83፡4-5 ከያህዌ ተለቅ ያለ የመዋጀት ዕቅድ ጋር እንዴት ይዛመዳል? ሰይጣናዊ ሙከራ አለወይ፣ የእግዚአብሔርን የመዋጀት ሥራ የሚገዳደር?

# መዝሙር 84
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የመቅደስ አምልኮን መናፈቅ<br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>ለመዘምራን አለቃ፤ የቆሬ ልጆች መዝሙር | በእግዚአብሔር ቤት የመኖር በረከት | ልጆች ጽዮንን ሲያመሰግኑ እንደ መናኞች ናፍቆት ግብ | የእግዚአብሔርን ቤት መናፈቅ | የምነና ልጆች |
| 84:1-4 | 84:1-2 | 84:1-2 | 84:1-4 | 84:1-2 |
| | 84:3-4 | 84:3-4 | | 84:3 |
| | | | | 84:4-5 |
| 84:5-7 | 84:5-7 | 84:5-7 | 84:5-7 | |
| | | | | 84:6-7 |
| 84:8-12 | 84:8-9 | 84:8-9 | 84:8-9 | 84:8-9 |
| | 84:10-11 | 84:10-12 | 84:10-12 | 84:10 |
| | | | | 84:11 |
| | 84:12 | | | 84:12 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ብዙዎች የሚገምቱት ይህ መዝሙር የተጻፈው በሌዋዊ ነው፣ በሆነ ምክንያት ከመቅደስ የታገደ።
1. በሕመም ምክንያት
2. በመገለል ምክንያት
3. ንጉሡ በመሸሹ የተነሣ (መዝ. 84፡9) ከእርሱ ጋር ከመሄዱ የተነሣ

ለ. በዚህ መዝሙር ላይ፣ ከእስራኤል አምላክ ጋር የሚሆነው ኅብረት የሚያያዘው ከመቅደስ ጋር ነው።
1. ያንተ ማደርያ ስፍራዎች፣ መዝ. 84:1ሀ – ቢ.ዲ.ቢ. 1015፣ መዝ. 43:3፤ 132:5
2. የያህዌ አደባባዮች፣ መዝ. 84:2a – ቢ.ዲ.ቢ. 346፣ መዝ. 65:4፤ 84:10፤ 96:8 100:4፤ 116:19፤ 135:2
3. መሠዊያዎችህ፣ መዝ. 84:3ሐ – ቢ.ዲ.ቢ. 258
4. ቤትህ፣ መዝ. 84:4ሀ
5. የጽዮን አውራ መንገዶች፣ መዝ. 84:5ለ፣ መዝ. 86:11፤ 122:1
6. በእግዚአብሔር ፊት ይሆናሉ፣ በጽዮን፣ መዝ. 84:7ለ፣ መዝ. 42:2፤ ዘጸ. 34:23፤ ዘዳ. 16:16
7. አደባባዮችህ፣ መዝ. 84:10ሀ፣ ዝከ. ቁ. 2
8. በአምላኬ በእግዚአብሔር ቤት መግቢያ ላይ ይቆማሉ (*ሔሶሀ*)፣ መዝ. 84:10ለ – ቢ.ዲ.ቢ. 706፣ ኬቢ. 765፣ *ሃዝሎል* ያልተወሰነ አወቃቀር (“የዘብ” አጠቃቀም፣ 1 ዜና. 23:5 ላይ)

ሐ. የተለያዩትን ስሞች/የመለኮትን መጠሪያዎች አስተውል።
1. የሠራዊት ጌታ (ያህዌ ጸባዖት)፣ መዝ. 84:1፣3፣12ሀ
2. ጌታ (ያህዌ) መዝ. 84:2ሀ፣8ሀ፣11ለ

3. ወዳጁ እግዚአብሔር (ኤል)፣ መዝ. 84:2ለ፣ ዘዳ. 5:26፤ መዝ. 42:2
4. ንጉሤ፣ መዝ. 84:3መ
5. አምላኬ (ኤሎሂም)፣ መዝ. 84:3መ
6. እግዚአብሔር (ኤል - ኤሎሂም፡ "የአማልክት አምላክ" ወይም በአናባቢዎች ለውጥ፣ "በእግዚአብሔር ፊት")፣ መዝ. 84:7ለ
7. ጌታ (ኤሎሂም) የሠራዊት፣ መዝ. 84:8ሀ
8. አምላክ (ኤሎሀ) የያዕቆብ፣ መዝ. 84:8ለ፣ መዝ. 46:7
9. እግዚአብሔር (ኤሎሂም)፣ መዝ. 84:9ሀ
10. አምላኬ (ኤሎሀ)፣ መዝ. 84:10ለ
11. ጌታ እግዚአብሔር (ያህዌ ኤሎሂም)፣ መዝ. 84:11ሀ

አብዛኞቹ የአሳፍ መዝሙሮች ብዙ ስሞች/መጠሪያዎች አሏቸው፣ የእግዚአብሔር። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች። እነዚህ እያንዳንዳቸው፣ እንዲሁም የእነርሱ ድብልቆች ለእስራኤላውያን የተለየ ፍች አላቸው።

መ. ይህ መዝሙር በብዙ መንገዶች ከመዝሙር 42 ጋር ይመሳሰላል። የቆሬ ልጆች፣ ባጠቃላይም የሌዋውያን ዘማሪያን ቤተሰቦች፣ ደግሞ ጽፈውታል። አባትየው ቆሬ ነው፣ በዳዊት ሥር የመዘምራን አለቃ። እነርሱም መዝሙር 42-49፤ 84-85፤ 87-88ን ጽፈዋል።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 84፡1-4**

**[1]የሠራዊት አምላክ ሆይ፥**
**ማደሪያዎችህ እንደምን የተወደዱ ናቸው!**
**[2]ነፍሴ የእግዚአብሔርን አደባባዮች ትወድዳለች ትናፍቅማለች**
**ልቤም ሥጋዬም በሕያው አምላክ ደስ ተሰኘ።**
**[3]ወፍ ለእርስዋ ቤትን አገኘች፥**
**ዋኖስም ጫጩቶችዋን የምታኖርበት ቤት አገኘች**
**የሠራዊት አምላክ ንጉሤም**
**አምላኬም ሆይ፥ እርሱ መሠዊያህ ነው።**
**[4]በቤትህ የሚኖሩ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው**
**ለዓለምና ለዘላለምም ያመሰግኑሃል። ሴላህ**

**84፡1 "የተወደዱ"** ይህ ቅጽል በጥሬው "የተወደደ" ነው (ቢዲቢ 391)። ኢየሩሳሌም፣ የታላቁ አምላክ ከተማ ውብ ነች፣ ከዚህ ሁሉ በላይ ግን "የተወደደች" ነች፣ እስራኤል (መዝ. 127፡2)።

▣ **"ማደሪያዎችህ"** ይህ ትይዩ ቅኔአዊ ግንኙነት አለው ከመዝ. 84፡2 ጋር። ስለዚህ፣ እሱ የሚያመለክተው የመቅደሱን አደባባዮች ነው በኢየሩሳሌም (መዝ. 43:3፤ 46:4)፣ እግዚአብሔር ራሱ ለማደሪያነት የመረጠው (ዘዳ. 12:5፣11፣14፣18፣21፣26፤ 14:23-25፤ 15:20፤ 16:2፣6፣11፣15፤ 17:8፣10፤ 18:6፤ 26:2፤ 31:11)።

**84፡2** ይህ ቁጥር ሦስት ግሦች አሉት፣ እነርሱም መዝሙረኛው ስለ እግዚአብሔር ምን እንደሚሰማው የሚገልጹ። እርሱም ከሌለኛው የቆሬ መዝሙር ጋር እጅግ ይመሳሰላል— መዝሙር 42 (ደግሞም መዝሙር 63ን ተመልከት)።

1. ነፍሴ ናፈቀች – ቢዲቢ 493፣ ኬቢ 490፣ ኒፋል የተጠናቀቀ
2. ነፍሴ ተመኘች – ቢዲቢ 477፣ ኬቢ 476፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 119:81
3. ልቤም ሥጋዬም በደስታ ዘመረች – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ ፒኤል IMየተጠናቀቀ፣ መዝ. 51:14

ይህ ስሜት-ነክ ቋንቋ እጅግ ኃይለኛ ነው። እርሱም የታማኝ ተከታዮችን አስደናቂ የስብዕና ጎን ያስታውሳል፣ ከእግዚአብሔር ጋር ባላቸው ኅብረት። ግቡ ከእርሱ ጋር መሆን ነው! እስራኤላውያን ከመቅደስ ጋር ተቆራኝተዋል። የአኪ አማኞች ከኢየሱስ ጋር ተቆራኝተዋል፣ ከአዲሱ መቅደስ (ዮሐንስ 2፡18-22)!

▣ **"ሕያው አምላክ"** ይህ የቃላት መለዋወጥ ነው፣ ለያህዌ ፍቺ ("ያለና የሚኖር ነኝ፣" ዘጸ. 3፡14)። የእስራኤል አምላክ ዘላለም የሚኖር፣ ብቸኛው ሕያው አምላክ ነው! (መዝ. 42፡2)።

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

**84፡3 "ወፍ"** ይህ ሁለት ነገሮችን የሚጠቅስ ሊሆን ይችላል፣ አንደኛው ጥሬአዊ ሌለኛው ተምሳሊታዊ። ተምሳሊታዊው የሚሆነው መዝሙረኛው በመቅደስ ወደ እግዚአብሔር ለመቅረብ መናፈቁ ነው— ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር። ትንሿ ረዳት የለሽ ወፍ ተምሳሊትነቷ ሰው ነው። ጥሬ ትርጉሙ የሚሆነውም ወፎች ነጻ ዕድል እንዳላቸው ነው፣ በመቅደስ በቅዱስ ስፍራዎች እንኳ።

▣ **"ንጉሤ"** ያህዌ እውነተኛው "ንጉሥ" ነው የኪዳኑ ሕዝብ (1 ሳሙ. 8፡7)። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ዲሞክራሲ አይደለም፣ ቲዎክራሲ እንጂ! ኢየሱስ ደኅና አድርጎ አስቀምጦታል፣ ሉቃስ 6፡46፣ "ስለምን 'ጌታ፣ ጌታ' ትሉኛላችሁ፣ የምናገራችሁን ሳታደርጉ?" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

**84:4 "በቤትህ የሚኖሩ ሁሉ የተመሰገኑ ናቸው"** ይህ መዝሙር የተዋቀረው "የተባረኩ" በሚለው ቃል ሦስት አጠቃቀሞች ዙርያ ነው (ቢዲቢ 80፣ መዝ. 84:4፣5፣12)። እሱም በመሠረቱ ፍችው "ደስታ" ማለት ነው (መዝ. 9:1)። እሱም በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የሚያመለክተው፣ ካህናትን ወይም እንግዶችን ነው (መዝ. 23:6፤ 27:4-6፤ 65:4)።

▣ **"ለዘላለም ያመሰግኑሃል"** ምስጋና የያህዌ እውነተኛ ተከታዮች ባሕርይ ነው (መዝ. 42:5፣11)። "ዘላለም" (ቢዲቢ 728) ዘወትር ጥቅም ላይ ውሏል፣ በዚህ የመዝሙር ክፍል (መዝ. 77:7፤ 78:17፣30፣32፤ 83:4)። ውስጣዊ ገጽታ አለው፣ ከእግዚአብሔር ጋር ላለ ኅብረት!

▣ **"ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 3:2 ላይ

***መዝሙር : 84:5-7***

**[5]አቤቱ፥ እርዳታው ከአንተ ዘንድ የሆነለት፥**
**በልቡም የላይኛውን መንገድ የሚያስብ ሰው ምስጉን ነው።**
**[6]በልቅሶ ሸለቆ ውስጥ በወሰነው ስፍራ**
**የሕግ መምህር በረከትን ይሰጣልና።**
**[7]ከኃይል ወደ ኃይል ይሄዳሉ**
**የአማልክት አምላክ በጽዮን ይታያል።**

▣ **"እንዴት ምስጉን ነው…"** ይህ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ ቃል ነው። "ምስጉን" (ቢዲቢ 80) በመዝሙር 26 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እንዲሁም 8 ጊዜ ምሳሌ ላይ። መዝ. 1:1 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"በልቡም የላይኛውን የጽዮንን መንገድ የሚያስብ"** ብዙዎቹ አታቾች (ኮሜንታተርስ) (እና ቢዲቢ) ይሄንን የሚተረጉሙት ወደ መቅደስ ለመድረስ የሚሄዱትን ተጓዦች (መናኞች) እንደሚጠቅስ ነው። ወንዶቹ አይሁድ ከ21 ዓመት ዕድሜ በላይ፣ እነርሱም ቀረብ ብለው የሚኖሩና የሚችሉ፣ በሦስቱ ዓመታዊ በዓላት መቅደስ ላይ እንዲገኙ ታዘዋል (ማለትም፣ ሌዋውያን 23 እና ዘጸአት 23)።

▣ **"የላይኛው መንገዶች"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 700) አስደናቂ የመመለስ ፍች አለው፣ በሁለቱም በሥጋዊ (ማለትም፣ ከስደት) እና መንፈሳዊ (ማለትም፣ የያህዌ ልዩ አዳኝ፣ መሲሕ መምጣት)።

ቀጣዩ የእኔ ማስታወሻ ነው ከኢሳይያስ 19:23።

**ኢሳይያስ 19:23** ነጻ ፍሰት ያለው እንቅስቃሴ ይኖራል፣ በአሕዛብ መካከል፣እግዚአብሔርን ለማምለክ ዓላማ። አሕዛብ መጥተዋል!

አስገራሚ የሚሆነው ኢሳይያስ ይሄንን የላይኛው መንገድ (አውራ መንገድ) ምናብ ብዙ ጊዜ መጠቀሙ ነው።

1. አውራ መንገድ በስደት ያሉት አይሁድ ይመለሱ ዘንድ፣ ኢሳ. 11:16፤ 57:14
2. አውራ መንገድ የአሕዛብ አምላኪዎች (ምዕመናን) ይመጡ ዘንድ፣ ኢሳ. 19:23
3. አውራ መንገድ የቅድስና፣ ኢሳ. 26:7፤ 35:8፤ 43:19፤ 49:11፤ 51:10
4. መሲሐዊው አውራ መንገድ፣ ኢሳ. 40:3፤ 42:16

**84:6 "ቤካ"** ቃሉ (ቢዲቢ 113) ፍችው "ማልቀስ" ማለት ነው። አንዳንዶች ይሄንን በጥሬው ወስደው ለኢየሩሳሌም ቅርብ ለሆነ ሸለቆ ጥቅም ላይ ያውሉታል (ማለትም፣ 2 ሳሙ. 5:22-24)። ሌሎች በተምሳሌታዊነት ይወስዱታል፣ ወደ ኢየሩሳሌም በሚደረግ ጉዞ (ምነና) ወይም ከስደት በመመለስ ጊዜ የሚያጋጥሙትን ችግሮች ለማሳየት።

▣ **"ምንጭ"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 745)፣ እንደ "ቤካ" በአንዳንዶች በጥሬው ይወሰዳል፣ እንደ ውኃ ስፍራ፣ በሌሎች ደግሞ እግዚአብሔር በጉዞ ላይ እንደሚያደርገው ክብካቤ ዘይቤ።

▣ **"ፊተኛው ዝናብ"** LXX እና ቫልጌት ይሄንን የሚተረጉሙት (ቢዲቢ 435) "የሕግ መምህር" በሚል ነው (አአመመቅ የኅዳግ ማስታወሻ ኢዩኤል 2:23 ላይ ያመለክታል)፣ እሱም የያህዌን የሲናዊ ኪዳን የሚጠቅስ (ዘጸአት 19-20)። በዚህ ዐውደ ጽሑፍ የሚያመለክተው የኢየሩሳሌምን መቅደስ ነው።

▣ **"በረከቶች"** ኤምቲ "በረከቶች" የሚል አለው (ቢዲቢ 139)፣ አኪጀት ግን "ኩሬ" የሚል አለው (ቢዲቢ 140)፣ እሱም "ምንጭ" ከሚለው ቃል ጋር ትይዩ የሆነ። ይህም የአናባቢን ለውጥ ብቻ ነው የሚያካትተው።

**84:7 "ከኃይል ወደ ኃይል"** አአመመቅ እነዚህን ቃላት የሚተረጉመው ለጉዞ ለሚደረጉ አቅርቦቶች ነው። ደግሞም እነዚህን ተናባቢዎች "ከከፍታ ወደ ከፍታ" በሚል መተርጎም ይቻላል፣ ፍችውም ከኮረብታ ወደ ኮረብታ፣ ወደ ኢየሩሳሌም ለመድረስ። አንዱ ተወዳጅ አታቼ (ኮሜንታተር) ዴሪክ ኪድነር፣ ቲንዳሌ የብሉ ሐተታዎች፣ ቅጽ 116፣ ገጽ 336፣ የሚለው፣ እሱ እንደሚያስበው፣ እሱ የሚጠቅሰው መንገደኞች የሚያድርባቸውን ደስታ ነው፣ ወደ መቅደስ በሚያደርጉት ጉዞ የመጨረሻው ምዕራፍ ላይ ሲደርሱ።

▣ ***"እያንዳንዳቸው* በእግዚአብሔር ፊት በጽዮን ይታያሉ"** እንደገና አአመመቅ እና አኪጀት ይሄንን የሚተረጉሙት እንደ መናኝ ጉዞ ነው። እነዚህን ተናባቢዎች መተርጎም ይቻላል "የአማልክት አምላክ (ኤል ኤሎሂም፣ አየተመቅ) በጽዮን ይታያል" (LXX፣ ፔሺታ)።

**መዝሙር ፡ 84፥8-12**

[8]**የሠራዊት አምላክ አቤቱ፥ ጸሎቴን ስማ**
**የያዕቆብ አምላክ ሆይ፥ አድምጥ። ሴላህ**
[9]**አቤቱ፥ መታመናችንን እይልን፥**
**ወደ ቀባኸውም ፊት ተመልከት።**
[10]**ከአእላፍ ይልቅ በአደባባዮችህ አንዲት ቀን ትሻላለች**
**በኃጥኣን ድንኳኖች ከመቀመጥ ይልቅ፥**
**በእግዚአብሔር ቤት እጣል ዘንድ መረጥሁ።**
[11]**እግዚአብሔር አምላክ ምሕረትንና እውነትን ስለ ወደደ፥**
**ሞገስንና ክብርን ይሰጣል**
**እግዚአብሔር በቅንነት የሚሄዱትን ከመልካም ነገር አያሳጣቸውም።**
[12]**የሠራዊት አምላክ ሆይ፥**
**በአንተ የታመነ ሰው ምስጉን ነው!**

**84፥8-9** አራት ተተኳሪዎች አሉ፣ በሁለት ትይዩ ስንኞች ጥቅም ላይ የዋሉ።

1. ስማ – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ ቃል
2. አድምጥ – ቢዲቢ 24፣ ኬቢ 27፣ ሂፊል
3. አቤቱ – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ ቃል
4. ተመልከት – ቢዲቢ 613፣ ኬቢ 661፣ ሂፊል

እነዚህ የጸሎት ጥያቄዎች ናቸው፣ ለያህዌ፣ ለመቅደስ አምልኮ ቀረቤታን እንዲመልስ። የመዝ. 84፥4-7 የብዙ ቁጥሮች ወደ መዝ. 84፥2-3 እንዴት የነጠላ ቁጥሮች እንዴት እንደተመለሱ ተገንዘብ።

መዝሙር 84፥8-9 ጸሎት ነው፣ ስለ ሰው ወደ መቅደስ አምልኮ መመለስ፣ በዚህም በእግዚአብሔር የእስራኤልን ንጉሥ ያበረታል ኃይልም ይሰጠዋል (መዝ. 84፥9ለ)!

**84፥8 "የሠራዊት አምላክ"** "ጸባኦት" (ቢዲቢ 838) ዘወትር ወታደራዊ ፍች ነው ያለው (ማለትም፣ ኢያሱ)፣ "እግዚአብሔር የሰማያዊው ሠራዊት አዛዥ።" በባቢሎናውያን አስትራል አምልኮተ ጣዖት ዐውደ-ጽሑፍ እሱ የሚያመለክተው "ከዋክብትን" ነው። ያህዌ የሰማያዊ ብርሃናት ሁሉ ፈጣሪና ተቆጣጣሪ ነው።

**84፥9 "ጋሻችን"** ይህ የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው (ዘፍ. 15:1፤ ዘዳ. 33:29፤ መዝ. 18:2፤ 115:9-11) ወይም የእስራኤል ንጉሥ።

▣ **"የቀባኸውም"** ይህ የሚያመለክተው ሊቀ-ካህኑን ነው (ሌዋ. 4፥3፤ ዘካርያስ 3-4)፣ ነገር ግን ንጉሡን ሊሆን ይችላል (መዝ. 2:2፤ 132:17፤ 1 ሳሙ. 2:35፤ 16:6፤ 2ሳሙ. 19:21)። መዝ. 89:18 ላይ ሁለቱም "ጋሻ" እና "ንጉሥ" ጥቅም ላይ የሚውሉት ለእስራኤል ንጉሥ ነው።

ለ "የተቀባው" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የብኪ መጠሪያዎች፣ የተለየው የሚመጣው።

**84፥10 "ከአእላፍ ይልቅ በአደባባዮችህ አንዲት ቀን ትሻላለች"** ይህ "እልፍ" የሚለው ቃል አጠቃቀም ነው፣ ተምሳሊታዊ በሆነ መንገድ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እልፍ [ኤልፍ])። ማወዳደሪያው ሙሉ ለሙሉ አልተቀመጠም፣ "ከያህዌ ጋር በመቅደሱ አንድ ቀን መሆን፣ አንድ ሺህ ቀናት ሌላ ስፍራ ለመሆን ይሻላል!" (ማለትም፣ መዝ. 27፥4)።

▣ **"ደጅ"** ርግጥ ነው በጥንታዊው ዓለም፣ ደጃፍ (ቢዲቢ 706) ይታይ የነበረው በአጋንንት እንደተሞላ ስፍራ ነበር፣ በተለይም በሮሜ ባህል። ሆኖም፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ግልጽ የሆነው ይህ አነጻጻሪ ዓረፍተ-ነገር መሆኑ ነው። መዝሙረኛው ከመቅደሱ ዳርቻ ቢሆን ይወዳል፣ ከኃጢአተኞች ምቾታዊና የድሎት ስፍራ ይልቅ።

አንዳንድ ኣታኞች "ደጃፍን" ለማድረግ ይሞክራሉ (ቢዲቢ 706) ለሌዋውያን በር ጠባቂዎች መጠሪያ ለማድረግ (1 ዜና. 9:19፣22፤ 2 ዜና. 23:4)። እንደሚመስለኝ "ደጃፍ" (መሳ. 19:27፤ 1 ነገ. 14:17፤ 2 ዜና. 3:7) ይህን ዐውደ-ጽሑፍ በተሻለ ይገጥማል።

▣ **"በኃጥኣን ድንኳኖች"** ይህ ከእስራኤል የዘላንነት ጊዜያት ተመልሶ የተጠቀሰ ነው። ተቃራኒው መዝ. 27፥5-6 ላይ ተገልጿል።

**84፥11 "ፀሐይ"** አራምኛ ታርጉም "ፀሐይ"ን የሚተረጉመው (ቢዲቢ 1039) "መከላከያ ግንብ" በሚል ነው ("ፀሐይ፣" שֶׁמֶשׁ፣ ቢዲቢ 1039፤ "የመከላከያ ምሽግ፣" שִׁמְשֹׁתַיִךְ ፣ ቢዲቢ 1039፤ ኢሳ. 54:12)። የመከላከያ ምሽግ ትይዩውን በተሻለ የሚገጥም ይመስላል፣ ጋሻን። ብኪ "ፀሐይ" የሚለውን ለመጠቀም አልፈለገም፣ ከያህዌ ጋር በተያያዘ፣ በስፋት ይመለክ በነበረው ፀሐይ ሳቢያ፣ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ)። "ፀሐይ" ዋነኛው ከሆነ፣ እንግዲያውስ እሱ ዘይቤ ነው፣ በብርሃን፣ እውነት፣ ጤና፣ ራዕይ፣ ባርኮት ወዘተ ላይ የሚያተኩር። መለኮት በዚህ መልኩ ተገልጿል ኢሳ. 60:19-20፤ ሚል. 4:2፤ ራዕ. 21:23 ላይ። እሱ እውነት ነው፣ የዘላለም ብርሃን።

**84፥11-12** ይህ የአማኝ ርዕዮተ-ዓለም ማጠቃለያ ነው። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ነው፣ ለእኛም፣ ምንም እንኳ በአካል ስሙ ከተጠራ የአምልኮ ስፍራ ብንነጠልም። ለታማኝ ተከታዮች ያህዌ

1. ፀሐይና ጋሻ ነው
2. ፀጋና ክብር ይሰጣቸዋል
3. ከመልካም ነገር አያሳጣቸውም (መዝ. 34፥10ለ)
4. እነርሱን ይባርካቸዋል (ሁኔታዊ ይዘት)
   ሀ. በቅንነት የሚሄዱ

ለ. የሚታመኑት

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙረኛው ለምን ከመቅደስ ራቀ?
2. ይህ መዝሙር ከመዝሙር 42 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
3. “የአውራ መንገዶች” መጠቀስ (መዝ. 84፡5) ጥሬአዊ ነው ተምሳሊታዊ?
4. መዝ. 84፡6 ለመተርጎም ለምን ይጠነክራል?
5. “የተቀባው” የሚለው ቃል (መዝ. 84፡9ለ) ማንን ነው የሚያመለክተው?
6. በምን መንገድ(ዶች) ነው ያህዌ “ፀሐይ”ን የሚመስለው? ይህ ምስያ ለምን በብኪ ያልተዘወተረ ነው?
7. ሁለቱን ሁኔታዎች ዘርዝር ፣ መዝ. 84፡11-12 ላይ የተጠቀሱትን። ኪዳኑ ሁኔታዊ ነው ወይስ ሁኔታዊ ያልሆነ?

# መዝሙር 85
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጸሎት ለእግዚአብሔር ምሕረት በሕዝብ ላይ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ። የቆሬ ልጆች መዝሙር | ጸሎት ጌታ ሞገስን ለምድሩ እንዲመልስ | ጸሎት ለመታደግ ከብሔራዊ ጠላት | ጸሎት ለሕዝቡ መልካምነት | ጸሎት ለሰላምና ለፍትሕ |
| 85:1-3 | 85:1-3 | 85:1-3 | 85:1-3 | 85:1-2<br>85:3 |
| 85:4-7 | 85:4-7 | 85:4-7 | 85:4-7 | 85:4-5<br>85:6-7 |
| 85:8-13 | 85:8-9<br>85:10-13 | 85:8-9<br>85:10-13 | 85:8-9<br>85:10-13 | 85:8-9<br>85:10-11<br>85:12-13 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ተገንዘብ
1. መዝ. 85፡1-3 ሁሉም የተጠናቀቁ እንዳሏቸው (ማለትም፣ የተጠናቀቀ ድርጊት፣ ዘወትር ያለፈ ጊዜ)
2. መዝ. 85፡4-7 ሁሉም ያልተጠናቁ እንዳሉት (ማለትም፣ በሂደት ላይ ያለ ድርጊት፣ የወቅቱ የያህዌ አቋም፣ ቁጣው በእስራኤል ላይ መሆኑን)
3. መዝ. 85፡5-6 ተከታታይ ሦስት ጥያቄዎችን መያዙን።

ለ. በርካታ ዋነኛ ሥነ-መለኮታዊ ቃላት ሰውኛ ዘይቤ ሆነዋል መዝ. 85፡10-13 ላይ (አዎንታዊ ኢሳ. 58፡8 ላይ፤ አሉታዊ ኢሳ. 59፡14-15 ላይ)።
1. ቸርነት፣ መዝ. 85፡10 — ልዩ ርዕስ፡ ቸርነት (ሄስድ)
2. እውነት/ታማኝነት፣ መዝ. 85፡10፣11 — ልዩ ርዕስ፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ እና ታማኝነት በብሉ
3. ጽድቅ፣ መዝ. 85፡10፣11፣13 — ልዩ ርዕስ፡ ጽድቅ
4. መዝ. 85፡10 (መዝ. 85፡8) — ልዩ ርዕስ፡ ሰላም (ብኪ)

ሐ. ምድሪቱ የሁለቱም ተጽዕኖ ዐርፎባታል፣ የአዎንታዊና አሉታዊ መንገዶች፣ የእግዚአብሔር ሕዝቦች በሚኖሩበት አገባብ (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)። የሰዎች ምርጫ ውጤት ይኖረዋል፣ ነገር ግን የያህዌ ጸጋና ምሕረት እንዲሁ ይሠራል!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 85፡1-3**

[1]**አቤቱ፥ ለምድርህ ሞገስን አደረግህ፥**
**የያዕቆብንም ምርኮ መለስህ።**
[2]**የሕዝብህን ኃጢአት አስቀረህ፥**
**አበሳቸውንም ሁሉ ከደንህ።**
[3]**መዓትህንም ሁሉ አስወገድህ**
**ከቍጣህ መቅሠፍት ተመለስህ።**

**85፡1-3** ጠንካራውን ትይዩ ተገንዘብ፣ እሱም የያህዌን ባሕርይና የማዳን ሥራ የሚጠቅሰውን።

1. ሞገስን አደረግህ – ቢ.ዲ.ቢ. 953፣ ኬ.ቢ. 1280፣ *ቃል የተጠናቀቀ*
2. ምርኮን መለስህ – ቢ.ዲ.ቢ. 996፣ ኬ.ቢ. 1427፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ *መዝ.* 14:7
   *ሀ.* ይቅርታ
   *ለ.* ወደ ከነአን መመለስ
3. በደልን ይቅር አልክ – ቢ.ዲ.ቢ. 669፣ ኬ.ቢ. 724፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
4. ኃጢአትን ሁሉ ከደንህ – ቢ.ዲ.ቢ. 491፣ ኬ.ቢ. 487፣ *ፒል* የተጠናቀቀ
5. መዓትህንም ሁሉ አስወገድህ – ቢ.ዲ.ቢ. 62፣ ኬ.ቢ. 74፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
6. ከቍጣህ መቅሠፍት ተመለስህ – ቢ.ዲ.ቢ. 996፣ ኬ.ቢ. 1427፣ *ሂፊል* የተጠናቀቀ፤ ተገንዘብ
   *ሀ.* ይሄው ተመሳሳይ ግሥ ቁ. 2 ላይ
   *ለ.* ተተኳሪ መልኩ፣ *መዝ.* 85፡4 ላይ
   *ሐ.* *ቃል* ያልተጠናቀቀው በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለው፣ *መዝ.* 85፡8 ላይ

ያህዌ የኪዳን ተስፋዎቹን ጠብቋል፣ የኪዳን ሕዝቡ የማይገባው በሆነበት ጊዜ እንኳ። ኃጢአት ውጤት አለው (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)፣ ነገር ግን ጸጋ ደግሞ የመጨረሻ ተጽዕኖ አለው፣ ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተነሣ (ዘጸ. 34:6፤ዘኍ. 14:18፤ ዘዳ. 4:31፤ ነህ. 9:27፤ መዝ. 86:15፤ 103:8፤ 145:8)!

**85፡1 "ምድርህ"** የእግዚአብሔር ሕዝብ የተገለጸባቸውን የተለያዩ መንገዶች ተገንዘብ።

1. ምድርህ፣ *መዝ.* 85፡1*ሀ*
2. ያዕቆብ፣ *መዝ.* 85፡1*ለ*
3. ሕዝብህ፣ *መዝ.* 85፡2*ሀ*

**85፡2 "ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝሙር 3፡2 ላይ።

**85፡3-4 "ሁሉ"** የ "ሁሉም" አጠቃቀም (ቢ.ዲ.ቢ. 481) ዋነኛ ነው። ኃጢአታቸው ሁሉ ተከድኗል፣ የእግዚአብሔር ቍጣ ሁሉ ተመልሷል። እንዴት ያለው አካታች መልካም ዜና ነው!

**85፡3 "ቁጣህ"** የያህዌን ምላሽ የሚጠቅሱትን የተለያዩ ቃላት ተገንዘብ፣ በሰው ልጅ አለመታዘዝ ላይ (መዝ. 78፡49)።

1. ቁጣ፣ *መዝ.* 85:3*ሀ* – ቢ.ዲ.ቢ. 720
2. የቍጣ መቅሠፍት፣ *መዝ.* 85:3*ለ* – ቢ.ዲ.ቢ. 354 አወቃቀር ቢ.ዲ.ቢ. 60 l
3. ቍጣ፣ *መዝ.* 85:4*ለ* – ቢ.ዲ.ቢ. 495
4. ተቆጣ፣ *መዝ.* 85:5*ሀ* – ቢ.ዲ.ቢ. 60፣ *ግሥ*
5. ቍጣ፣ *መዝ.* 85:5*ለ* – ቢ.ዲ.ቢ. 60፣ ስም

እነዚህ የእግዚአብሔር ባሕርይ የተለያዩ ገለጻዎች ናቸው

1. *መዝ.* 85:1-2
2. *መዝ.* 85:10-12

**መዝሙር ፡ 85፡4-7**

[4]**የመድኃኒታችን አምላክ ሆይ፥ መልሰን፥**
**ቍጣህንም ከእኛ መልስ።**
[5]**በውኑ ለዘላለም ትቈጣናለህን?**
**ቍጣህንስ ለልጅ ልጅ ታስረዝማለህን?**
[6]**አቤቱ፥ ትመለሳለህ ታድነንማለህ**
**ሕዝቡም በአንተ ደስ ይላቸዋል።**
[7]**አቤቱ፥ ምሕረትህን አሳየን፥**
**አቤቱ፥ መድኃኒትህንም ስጠን።**

**85፡4-7** ይህ አንጓ በሁለት የጸሎት ጥያቄዎች ይጀምራል ("መልሰን" – ቢ.ዲ.ቢ. 996፣ ኬ.ቢ. 1427፣ *ቃል* ተተኳሪ፤ "አስወግድ" – ቢ.ዲ.ቢ. 830፣ ኬ.ቢ. 974፣ *ሂፊል* ተተኳሪ) በጸሎት ጥያቄም ይጨርሳል ("አሳይ" – ቢ.ዲ.ቢ. 906፣ ኬ.ቢ. 1157፣ *ሂፊል* ተተኳሪ)።

ከዚያም በኋላ ተለጣጣቂ ጥያቄዎች የሚከተሉት ይሆናሉ፣ ከመመለሱ (ተሓድሶ) ጥሪ ጋር የተያያዙ።

1. ለዘላለም ትቆጣናለህን? *መዝ.* 74:1፤ 79:5፤ 80:4

2. ቍጣህንስ ለልጅ ልጅ ታስረዝማለህን?
3. ተመልሰህ ታድነንማለህን? መዝ. 71:20፤ 80:18

እስራኤላውያን ሊገባቸው አልቻለም፣ እንዲወረሩና እንዲጋዙ ያህዌ ለምን እንደፈቀደ (ዕንባቆም 1)! እነርሱ የእርሱ ሕዝቦች ናቸው፣ በዚህ ዓለም ላይም የእርሱ ምስክሮች። ችግሩ የኪዳን አለመታዘዝ ነው። የተሳሳተው መልእክት ከአሕዛብ ጋር እንዲከናወን ተደረገ (ሕዝ. 36፡22-36)።

**85፡7 "ምሕረት"** ማስታወሻ ተመልከት፣ ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት፣ ለ ላይ።

▣ **"ማዳንህ"** መዝ. 85፡4 ላይ መዝሙረኛው ያህዌን ይጣራል "አምላክ ሆይ (ኤሎህ) የመድኃኒታችን" (ቢ.ዲ.ቢ. 447)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መዳን (ብኪ)።

### መዝሙር ፡ 85፡8-13

**[8]እግዚአብሔር አምላክ የሚናገረውን እሰማለሁ**
**ሰላምን ለሕዝቡና ለቅዱሳኑ**
**ልባቸውንም ወደ እርሱ ለሚመልሱ ይናገራልና።**
**[9]ነገር ግን ክብር በምድራችን ያድር ዘንድ**
**ማዳኑ ለሚፈሩት ቅርብ ነው**
**[10]ምሕረትና እውነት ተገናኙ**
**ጽድቅና ሰላም ተስማሙ።**
**[11]እውነት ከምድር በቀለች፥**
**ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተች።**
**[12]እግዚአብሔርም በጎ ነገርን ይሰጣል፥**
**ምድራችንም ፍሬዋን ትሰጣለች።**
**[13]ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል፥**
**ፍለጋውንም በመንገድ ውስጥ ያኖራል።**

**85፡8-12** ይህ አንዳ ለመዝሙረኛው ጸሎት ምላሽ ነው። እግዚአብሔር እንዲናገረው ፈልጓል ("እሰማለሁ" ቢ.ዲ.ቢ. 1033፣ ኬ.ቢ. 1570፣ *ቃል ተጓዳኝ*)። መልእክቱን/ራዕዩን ያስተላልፋል።

1. ሰላም ይሁን
   ሀ. ለሕዝቡ
   ለ. ለቅዱሳኑ (ቢ.ዲ.ቢ. 339)
2. ማዳኑ ቅርብ ነው
3. በምድራቸው ላይ ግርማው ይኖራል (ማለትም፣ የያህዌ አካላዊ መገኘት፣ እንደ ሼከናህ ደመና፣ እዚህ ግን በመቅደስ ውስጥ፣ መዝ. 63:2፤ 102:15-16)
4. ምሕረት እና እውነት ተገናኙ
5. ጽድቅ እና ሰላም ተስማሙ
6. እውነት ከምድር በቀለች
7. ጽድቅም ከሰማይ ተመለከተች
8. እግዚአብሔር በጎ ነገርን ይሰጣል
9. ጽድቅ በፊቱ ይሄዳል

ሁኔታዎቹን ግን ተገንዘቡ።

1. ወደ ስንፍና እንዳይመለሱ (ቢ.ዲ.ቢ. 493)— ቢ.ዲ.ቢ. 996፣ ኬ.ቢ. 1427፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. እሱን ለሚፈሩ/ለሚያከብሩ (ልዩ ርዕስ፡ መፍራት)

እሱም ሊሆን ይችላል "ለቅዱሳኑ" መዝ. 85፡8ለ ደግሞ የሰላም ሁኔታ ነው። ምንም ዓይነት ሰላም አይኖርም ከእግዚአብሔር ጋር ከሚኖር ትክክለኛ ግንኙነት በቀር፣ እና ከዚያም ከሌሎች ጋር።

ደግሞም መዝ. 85:11 የሚናገረው ስለ ታማኝነት ነው፣ ስለ እግዚአብሔር ጽድቅ ሁኔታዊነት (ማለትም፣ እግዚአብሔር ራሱ) ከሰማይ ሲመለከት።

መዝሙር 85:10-11 ብርቱ ምናባዊ ምስያ ነው፣ ለእግዚአብሔር ማንነት። እነዚህ አስተዋጽዖዎች ሰውኛ ዘይቤ ሆነዋል፣ አንድ ላይ እንደሚመጡ ዓላማውን ለማስፈጸም።

1. ከግዞት መመለስ
2. ድርቁን ማስቀረት
3. የፍጻሜ ዘመን ዳርቻ (የማጠቃለያ ርምጃ) (ልዩ ርዕስ፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)

**85፡8 "ጌታ እግዚአብሔር"** ይህ ኤል ሲደመር ያህዌ ነው። እሱም ዘወትር ያህዌ ኤሎሂም ነው፣ ዘፍ. 2፡4 ላይ እንዳለው (ያህዌ ኤሎሂም)። አኢ.መቅ እነዚህን ሁለት የአምላክ ስሞች የሚመለከታቸው ትይዩ ስንኞችን እንደሚያስተዋውቁ ነው።

"የእግዚአብሔር መልእክት ምንድነው?"
"የያህዌ መልእክት ሰላም ነው።"

ተመሳሳይ አገባብ ኤቢን ይከተለዋል (ገጽ 285)።

▣ **"እነርሱ ግን ወደ ስንፍና እንዳይመለሱ"** ይህ ሔምቲን ያንጸባርቃል። LXX ሐረጉን የሚረዳው "ልባቸውን ወደ እርሱ ለሚመልሱ ለእነርሱ" በሚል ነው። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 345) ለሔምቲ "ሐ" ደረጃ ይሰጣል (ማለትም፣ ሁነኛ ጥርጣሬ)።

**85፥12** የግብርና በረከት ተስፋ ከኪዳን ታማኝነት ጋር ይተሳሰራል (ማለትም፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)። ኤቢ መዝሙሩን የሚመለከተው እንደ ቅድመ-ግዞት የዝናብ ጥሪ ነው፣ በድርቅ መሐል። የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 1377) መዝሙሩን የሚመለከተው የእግዚአብሔር ሕዝብ ወደ ከነአን እንዲመለስ እንደሚደረግ ልመና ነው። ይኽም የተመሠረተው

1. "መሬት" መዝ. 85፥1፣ 9-12 ላይ
2. "የበረከቱ መመለስ፣" ኤር. 30፥3፣18 ላይ ጥቅም ላይ የዋለ፤ አሞጽ 9፥14
3. መዝ. 85፥7፣ ወደ ተመለሰው መቅደስ ያመለክታል

▣ **"በጎ ነገር"** ይህ ምንድር ነው የሚያመለክተው?

1. ማዳን — ዘጸ. 18፥9
2. ባርኮት – መዝ. 34፡10
3. ከነአን – ዘጸ. 3፡8፤ ዘዳ. 1፡35፤ 3፡25፤ 4፡21-22፤ 8፡7፣10፤ ኢያ. 23፡13
4. ወሰን የሌለው በጎነት ከያህዌ፣ ኪዳኑን በሚጠብቁት ላይ — መዝ. 84፥11

ምናልባትም ሆን ተብሎ የተደረገ አሻሚነት፣ ማለትም፣ የእግዚአብሔር ረድኤት በእያንዳንዱ አስፈላጊ ስፍራ። እዚህ፣ የግብርና በረከት (ምርት) (መዝ. 67፥6)።

**85፥13** ብኪ ዘወትር የ "መንገድ፣"ን "ፈለግ፣"ን "አውራ መንገድን" ምስያ የሚመለከተው የእግዚአብሔርን እና የሰዎችን ድርጊቶች ለማሳየት ነው፣ (ማለትም፣ መዝ. 25፡4፣8፣9፣10፣12፣15)። መንፈሳዊ ሕይወት እንደ "መንገድ" ተመልክቷል!

ጽድቅም እንደገና ሰውኛ ዘይቤ ሆኗል (መዝ. 85፡10-11) እንደ አዋጅ (መዝ. 85፡8) በእስራኤል ፊት እንደሚሄድ፣ የያህዌን የፍቅር፣ ክብካቤ፣ ጥበቃ፣ እና ከሕዝቡ ጋር መገኘት ምስራቹን ለማሰማት፣ ከስደት ወይም ከድርቅ በኋላ። ጀሮም የመጽሐፍ ቅዱስ ሐተታ (ኮሜንተሪ) (ገጽ 591) እሱን የሚመለከተው እንደ ፍጻሜው ማጣቀሻ ሊሆን ይችላል።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ታሪካዊውን መቼት ማግኘት ይቻላልን? እንደዚያ ከሆነ፣ ሦስቱን አማራጮች ዘርዝር?
2. የመዝ. 85፥1-2 ግሦች ከመዝ. 85፥3 ግሦች ጋር እንዴት ይዛመዳሉ?
3. መዝ. 85፥8 መዝሙረኛውን ነው የሚያመለክት ወይስ ነቢይን?
4. መዝ. 85፥10-11 እንዲህ ዓይነት ብርቱ፣ አነቃቂ፣ አበረታች ምናባዊ ምስያ እንዴት ሆነ?
5. መዝ. 85፥11 ከመለኮታዊ ሉዓላዊነት እና ከሰው ነጻ ፍቃድ ጋር እንዴት ይገናኛል?
6. "በጎ" የሚለውን መዝ. 85፥12 ላይ ግለጽ።
7. "የመንገድን" ወይም "ፈለግን" ምናባዊ ምስያ አብራራ።

# መዝሙር 86
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የዕርዳታና የመታመን ጸሎት<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት ጸሎት | የምሕረት ጸሎት፣ ከጌታ ክብር ምልጃ ጋር | ጸሎት ከግል ጠላቶች ለመታደግ | የዕርዳታ ጸሎት | በችግር ጊዜ ጸሎት (የስንኝ ቁጥሮች ከLXX) |
| 86:1-5 | 86:1-5 | 86:1-7 | 86:1-2 | 86:1-2ለ |
| | | | | 86:2ሐ-4 |
| | | | 86:3-5 | |
| | | | | 86:5-6 |
| 86:6-10 | 86:6-7 | | 86:6-7 | |
| | | | | 86:7-8 |
| | 86:8-10 | 86:8-11 | 86:8-10 | |
| | | | | 86:9-10 |
| 86:11-13 | 86:11-13 | | 86:11-13 | 86:11 |
| | | 86:12-13 | | 86:12-13 |
| 86:14-17 | 86:14-15 | 86:14-17 | 86:14-17 | 86:14 |
| | | | | 86:15-16ሀ |
| | 86:16-17 | | | 86:16ለ-17 |
| | | | | 86:18 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ የሚመደበው "ከግለሰባዊ ሰቆቃ" ጋር ነው። የያህዌ ጻድቅ ተከታይ፣ ጻድቅ አምላኩ በእርሱ አኳያ እንዲሠራ ጥሪ ያቀርባል።
1. ጻድቅ ፈጣሪ፣ መዝ. 86:1፣2፣3፣4
2. ጻድቅ አምላክ፣ መዝ. 86:5፣6

ለ. ይህ መዝሙር አስደናቂ ሁለንተናዊ ይዘት አለው፣ መዝ. 86:9 ላይ (መዝ. 22:27፤ 46:10፤ 47:9፤ 57:5፣11፤ 64:9፤ 65:8፤ 66:1-7፤ 67:2-5፤ 98:23፤ 99:2-3 102:15)። ይህ ቁጥር የመስቀልያው ሥነ-መለኮታዊ ማዕከል ነው (ማለትም፣ የዕብራይስጥ ቅኔአዊ አወቃቀር)።

ሐ. ታሳቢው የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር ሊሆን የሚችለው፡
1. የደራሲው ሥነ-መለኮታዊ ይግባኝታ፣ መዝ. 86፡1-7
2. የውዳሴ መዝሙር ለእግዚአብሔር፣ መዝ. 86፡8-10
   ሀ. የእርሱ ወሰን የለሽነት

ለ. የእርሱ የተለየነት (አሀዳዊነት)
3. የውዳሴ መዝሙር ለእግዚአብሔር፣ መዝ. 86፥11-17፣ ለእርሱ ወሰን የለሽነት

መ. 15 ተተኳሪ ጥያቄዎች እዚህ መዝሙር ላይ ይገኛሉ።
1. ጆሮህን አዘንብል፣ መዝ. 86:1 – ቢ.ዲ.ቢ. 639፣ ኬ.ቢ. 692፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 17:6፤ 31:2፤ 71:2፤ 102:2፤ ተመሳሳይ ግሥ በአልተጠናቀቀ፣ መዝ. 88:2 ላይ
2. ስማኝ፣ መዝ. 86:1 – ቢ.ዲ.ቢ. 772፣ ኬ.ቢ. 851፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. ነፍሴን ጠብቃት፣ መዝ. 86:2 – ቢ.ዲ.ቢ. 1036፣ ኬ.ቢ. 1581፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 25:20
4. አድን፣ መዝ. 86:2 – ቢ.ዲ.ቢ. 446፣ ኬ.ቢ. 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 28:9፤ 31:16፤ 59:2፤ 71:2
5. እራራልኝ፣ መዝ. 86:3 – ቢ.ዲ.ቢ. 335፣ ኬ.ቢ. 334፣ *ቃል ተተኳሪ*
6. ነፍሴን ደስ አሰኛት፣ መዝ. 86:4 – ቢ.ዲ.ቢ. 970፣ ኬ.ቢ. 1333፣ *ፒል ተተኳሪ*
7. ስማኝ፣ መዝ. 86:6 – ቢ.ዲ.ቢ. 24፣ ኬ.ቢ. 27፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
8. ተመልከተኝ፣ መዝ. 86:6 – ቢ.ዲ.ቢ. 904፣ ኬ.ቢ. 1151፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
9. አስተምረኝ፣ መዝ. 86:11 – ቢ.ዲ.ቢ. 34፣ ኬ.ቢ. 436፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 25:4፣12፤ 27:11
10. ልቤን አጽና፣ መዝ. 86:11 – ቢ.ዲ.ቢ. 402፣ ኬ.ቢ. 405፣ *ፒል ተተኳሪ*
11. ወደ እኔ ተመለስ፣ መዝ. 86:16 – ቢ.ዲ.ቢ. 815፣ ኬ.ቢ. 937፣ *ቃል ተተኳሪ*
12. እራራልኝ፣ መዝ. 86:16 – እንደ ቁ. 5 ያለ
13. ኃይልን አጽናልኝ፣ መዝ. 86:16 – ቢ.ዲ.ቢ. 678፣ ኬ.ቢ. 733፣ *ቃል ተተኳሪ*
14. አድን፣ መዝ. 86:16 – እንደ ቁ. 4 ያለ
15. ምልክትን አሳየኝ፣ መዝ. 86:17 – ቢ.ዲ.ቢ. 793፣ ኬ.ቢ. 889፣ *ቃል ተተኳሪ*

ሠ. ስም ጠቃሾቹን ተገንዘብ።
1. ጌታ ሆይ (ያህዌ) መዝ. 86:1፣ 3፣ 6፣ 11፣ 17
2. አቤቱ አንተ አምላኬ (*ኤሎሀ*)፣ መዝ. 86:2
3. ጌታ ሆይ (*አዶን*)፣ መዝ. 86:4፣ 5፣ 8፣ 9፣ 15
4. አምላክ ሆይ (*ኤሎሂም*)፣ መዝ. 86:10፣14
5. አቤቱ ጌታ አምላኬ (*ኤሎሀ*)፣ መዝ. 86:12፤ *ኤሎሀ* ደግሞ መዝ. 86:2 ላይ
6. አቤቱ ፍርድ (ስም/መጠሪያ የለውም) ሰጪ፣ መዝ. 86:16ለ

ሌሎች ስሞች/መጠሪያዎች ጥቅም ላይ የዋሉት
1. እግዚአብሔር (*ኤል*)፣ መዝ. 86:15
2. ስምህ (ቢ.ዲ.ቢ. 1027)፣ መዝ. 86:9፣ 11፣ 12

እነዚህ ሁሉ ብርቱ ጸሎትን ያንጸባርቃሉ፣ ለእስራኤል አምላክ ዕርዳታ!

ረ. ተናጠላዊውን የመዝሙር መዋቅር ለመመደብ ያስቸግራል። ይህ መዝሙር መስቀልያዊ ከሆነ (አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ ገጽ 829 ተመልከት)፣ እንግዲያውስ መዝ. 86፡9 ማዕከላዊው ቁልፍ ቁጥር ነው። ለእኔ መዝ. 86፡8 ከሥነ-መለኮት አኳያ ቁልፍ ቁጥር ነው፣ እንዲሁም መዝ. 86፡9 ሎጂካዊ ተቀጥያው ነው። አሀዳዊነት የእስራኤል የተለየነት ነው በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) (ከሁለት አጫጭር የተለዩዎች ጋር፣ አንዱ ግብፅ ውስጥ አንደኛው አሦር ውስጥ)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ፣ እና ልዩ ርዕስ፡ አሀዳዊነት።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 86፥1-5**

**[1]አቤቱ፥ ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል አድምጠኝም፥**
**ችግረኛና ምስኪን ነኝና።**
**[2]ቅዱስ ነኝና ነፍሴን ጠብቅ**
**አምላኬ ሆይ፥ አንተን የታመነውን ባሪያህን አድነው።**
**[3]አቤቱ፥ ቀኑን ሁሉ ወደ አንተ እጮኻለሁና ማረኝ።**
**[4]የባሪያህን ነፍስ ደስ አሰኛት፥**
**አቤቱ፥ ነፍሴን ወደ አንተ አነሣለሁና።**
**[5]አቤቱ፥ አንተ መሐሪና ይቅር ባይ ነህና፥**
**ምሕረትህም ለሚጠሩህ ሁሉ ብዙ ነውና።**

**86፥1 "አዘንብል"** ይህ ዘይቤ ነው "መጎብጥ" ወይም "መዞር" ከሚለው ግሥ የተገኘ (ቢ.ዲ.ቢ. 639፣ ኬ.ቢ. 692)። እሱም ያህዌን ይጣራል፣ የባርያውን ልመና እንዲሰማ (መዝ. 86:3፣4፣6፣7)።

▣ **"ጌታ ሆይ"** ይህ ያህዌ ነው (ማለትም፣ ስሙ ዘጸ. 3፥14 ላይ ተገልጿል፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች)። ይህም የመለኮት የኪዳን ስም ነው። እሱ "የመሆን ግሥ" ዓይነት ነው።

የቃላት መዘዋወር (ጨዋታ) አለ፣ በያህዌ እና (መዝ. 86:1፣3፣6፣11)፣ *ኤሎሂም* (መዝ. 86:2፣10፣12) በ*አዶን* መካከል (መዝ. 86:4፣8፣ 9፣ 12)። እነዚህም የመለኮትን የተለያዩ ጽንሰ-ሐሳቦች ይወክላሉ።

1. ያህዌ — እግዚአብሔር እንደ አዳኝ፣ ተቤዢ
2. ኤሎሂም — እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ፣ ደጋፊ፣ መጋቢ
3. አዶናይ — እግዚአብሔር እንደ ጌታ፣ ባለቤት፣ ባል

▣ **"መልስ"** ይህ የመረጃ ጸሎት አይደለም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር አካላዊ መገኘትና ክብካቤ ዋስትና እንጂ። መዝሙረኛው ይሄንን ተለማምዶታል፣ እናም በሆነ ምክንያት አሁን አልሆነም! እሱም ለእግዚአብሔር ልመና ነው በሚታይ መንገድ እንዲሠራ።
1. እንዲያድን (መዝ. 86፡7)
2. እንዲመሰክር (መዝ. 86፡8-10)

▣ **"እኔ ችግረኛና ምስኪን ነኝና"** ይህን ሐረግ (ቢዲቢ 776 እና ቢዲቢ 2) መረዳት የሚገባው በመንፈሳዊ መልኩ ነው፣ ታማኝ ቅሬታን (የቀረ) ለመጥቀስ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቅሬታ፣ በሦስት መልኩ፣ መዝ. 34፡6፤ 35፡10፤ 40፡17፤ 70፡5)። በዚህ መዝሙር ላይ እሱ የሚያመለክተው ንጉሡን ነው።

**86፡2 "ቅዱስ ነኝና ነፍሴን ጠብቅ"** ሁለት ቃላት አሉ፣ መዝሙረኛውን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉ።
1. ነፍስ – ኔፊሽ ፥ ቢዲቢ 659፣ መዝ. 86:4 (ሁለቴ)፣ 13፣14፤ ማስታወሻውን በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ላይ ተመልከት መዝ. 3:2 እና ዘፍ. 35:18 ላይ
2. ቅዱስ የሆነ/ሰው – ቢዲቢ 339፣ ማስታወሻውን በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ላይ ተመልከት መዝ. 16:10፤ 50:5 ላይ

ይህም ተከታታይ ምክንያቶችን ይዘረዝራል፣ እግዚአብሔር ለምን በመዝሙረኛው አኳያ እንደሚሠራ።
1. እሱ ቅዱስ በመሆኑ፣ መዝ. 86፡2 (ሄሲድ፣ ቢዲቢ 339፣ ለኪዳኑ ታማኝ፣ ከሄሲድ ጋር የተዛመደ፣ ቢዲቢ 339)
2. በያህዌ ስለሚያምን፣ መዝ. 86፡2
3. ለያህዌ ስለሚጸልይ፣ መዝ. 86፡3፣4፣5
4. እግዚአብሔርም ደግሞ ሄስድ ስለሆነ፣ መዝ. 86፡5፣15.

ብኪ ላይ፣ ሞት ከእግዚአብሔር ጋር ዳግም እንደመገናኘት ተደርጎ አይወሰድም ነገር ግን እንደ ጸጥታና ደስታ-የለሽ ስፍራ እንጂ። መዝሙረኛው እግዚአብሔርን በአምልኮ ማወደስ ይፈልጋል። ከዚህ ሕይወት በኋላ ምን እንደሚሆን ያለው ጽንሰ-ሐሳብ ጎልብቷል (ማለትም፣ ቀጣይነት ያለው መገለጥ) አኪ ላይ። እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣ ስለ ኢየሱስና ስለ አዲስ ኪዳን!

▣ **"አድን"** በብኪ ይህ የሚያመለክተው አካላዊ ትድግናን (መታደግ) ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት (ብኪ)።

▣ **"ባንተ የሚታመነውን"** ማስታወሻውን በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ላይ ተመልከት መዝ. 4፡5።

**86፡3 "ቀኑን ሁሉ ወደ አንተ እጮኻለሁ"** ይህ የሚያመለክተው በቀኑ ውስጥ የሚደረገውን ጸሎት ነው (መዝ. 22:2፤ 25:5፤ 88:9)።

**86፡4 "ነፍሴን አነሣለሁ"** ይህ ፈሊጥ ነው፣ ለያህዌ የኃይል ስፍራ እውቅና የመስጠት (ማለትም፣ በከፍታ፣ በሰማይ፣ መዝ. 123:1) እና የአንዱን አጠቃላይ ማንነት ለእርሱ የማቅረብ (መዝ. 25:1፤ 143:8፤ ሰቆ. 3:41)።

ባህላዊው ዳራ ሊሆን የሚችለው
1. መሥዋዕቶች ወደ ያህዌ እንደሚነሡ
2. የአይሁድ ጸሎት የሚደረገው ራስ፣ ዓይኖች፣ እና እጆች ወደ ሰማይ ተነሥተው ነበር

**86፡5** ይህ የያህዌ ባሕርይ ማጠቃለያ ነው (መዝ. 86:10፣15)። የዚህ ዓይነት ማጠቃለያዎች ብኪ ውስጥ በብዛት ይገኛሉ (ዘጸ. 34:6፤ ዮናስ 4:2፤ ነህ. 9:17፤ ኢዩኤል 2:13፤ መዝ. 86:15፤ 103:8፤ 145:8)።

የሰው ተስፋ ያለው በተደራጀው፣ በአፍቃሪው በያህዌ ባሕርይ ላይ ነው። እሱም
1. መልካም ነው – ቢዲቢ 373 II (1 ዜና. 16:34፤ 2 ዜና. 5:13፤ 7:3፤ 30:18፤ ዕዝራ 3:11፤ መዝ. 25:8፤ 34:8፤ 100:5፤ 106:1፤ 107:1፤ 118:1፣25፤ 135:3፤ 136:1፤ ኤር. 33:11፤ ነህ. 1:7)
2. ይቅር ሊል ዝግጁ ነው – ቢዲቢ 699፣ ቅጽል እዚህ ብቻ ነው የሚገኘው (ነህ. 9:17፤ መዝ. 130:4 ለተዛማጅ ስም አጠቃቀም)
3. ቸርነቱ የተትረፈረፈ – ቢዲቢ 912 I አወቃቀር ቢዲቢ 338 (ዘጸ. 34:6፤ ነህ. 9:17፤ መዝ. 103:8፤ 145:8፤ ኢዩኤል 2:13፤ ዮና. 4:2)፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: ቸርነት (ሄሲድ)
4. ታላቅ፣ መዝ. 86:10 – ቢዲቢ 152 (መዝ. 77:13)
5. ድንቅ ነገሮችን ያደርጋል፣ መዝ. 86:10 – ቢዲቢ 810፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: ድንቅ ነገሮች
6. መሐሪ፣ መዝ. 86:15 – ቢዲቢ 933
7. ቸር፣መዝ. 86:15 – ቢዲቢ 337
8. ለቁጣ የዘገየ፣ መዝ. 86:15 – ዝከ. ተመሳሳይ ትይዩ ግሦች እንደ ቁ. 3
9. ታማኝነቱ/እውነቱ የበዛ፣ መዝ. 86:15 – ዝከ. ተመሳሳይ ትይዩ ግሦች እንደ ቁ. 3

▣ **"አንተን ለሚጠሩህ ሁሉ"** የያህዌ የፍቅሩና የመቀበሉ ስጦታ ዳርቻ አስገራሚ ነው፣ በብኪ መዝሙር ላይ። ተመሳሳይ ሁለንተናዊ ተስፋ መዝ. 86፡9 ላይ ተደግሟል። እግዚአብሔር በእንኳን ደኅና መጣችሁ ይቀበላል፣ በእምነትና በአምልኮ የሚቀርቡትን ሁሉ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

እግዚአብሔርን "መጥራት" የእምነት ድርጊት ነው፣ በአደባባይ አምልኮ ላይ የሚገለጽ፣ ኢዩኤል 2፡32 ላይ እና በጳውሎስ ሮሜ. 10፡9-13 ላይ ተጠቅሷል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "መቀበል፣" "ማመን፣" "መመስከር/መተንበይ፣" እና "መጥራት" ምን ማለት ነው?

***መዝሙር ፡ 86፥6-10***

**[6]አቤቱ፥ ጸሎቴን አድምጥ፥**
**የልመናዬንም ድምፅ ስማ።**
**[7]ትመልስልኛለህና**
**በመከራዬ ቀን ወደ አንተ እጠራለሁ።**
**[8]አቤቱ፥ ከአማልክት የሚመስልህ የለም፥**
**እንደ ሥራህም ያለ የለም።**
**[9]ያደረግሃቸው አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ፥ አቤቱ፥ በፊትህም ይሰግዳሉ፥**
**ስምህንም ያከብራሉ**
**[10]አቤቱ፥ ድንቅ የምታደርግ አንተ ታላቅ ነህና፥**
**አንተም ብቻህን ታላቅ አምላክ ነህና።**

**86፥6-7** እነዚህ ከመዝ. 86፥1 ጋር ትይዩ ናቸው። እነርሱም መዝሙረኛው በእግዚአብሔር አካላዊ መገኘትና ክብካቤ ላይ ያለውን መተማመን የሚገልጹ ናቸው።

**86፥7 "*በመከራዬ ቀን*"** መዝሙረኛው ያለበት ፈታኝ ሁኔታ መዝ. 86፥14 ላይ ተገልጿል። እነዚህ ጠላቶች በበርካታ መንገዶች ተገልጸዋል።

1. ትዕቢተኛ ሰዎች በእኔ ላይ ተነሥተዋል
2. የከፉ ሰዎች ጉባኤ ሕይወቴን ሊይዛት ነው (ኔፊሽ፣ የድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ማስታወሻውን ተመልከት፣ ዘፍ. 35፥18 ላይ)
3. በፊታቸው አላኖሩህም
4. የሚጠሉኝ፣ መዝ. 86፥17ለ

**86፥8 "*የሚመስልህ የለም*"** ይህ የአሀዳዊነት ማረጋገጫ ነው (መዝ. 86፥10ለ)፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት። ይህም ዘጸ. 15፥11ን ያንጸባርቃል።

▣ **"ከአማልክት"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ኤሎሂም ነው፣ ለመንፈሳዊ ሕላዌዎች (መላእክት) ጥቅም ላይ የዋለ። ቃሉ ደግሞ ለሰው ፈራጆች ጥቅም ላይ ውሏል፣ ብኪ ላይ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ ***"እንደ ሥራህም ያለ የለም።"*** ያህዌ የፍጥረት አምላክ ነው። እሱ ብቸኛው ፈጣሪ ነው፣ ሌሎች ሁሉ ሕላዌዎች ተፈጥረዋል። እሱ የሚሠራ አምላክ ነው። የአሕዛብ ጣዖታት ሊያዩ፣ ሊሰሙ፣ ወይም ሊሠሩ አይችሉም!

**86፥9 "*ያደረግሃቸው አሕዛብ ሁሉ ይመጣሉ፥*"** አንድ ፈጣሪ አምላክ ብቻ ካለ፣ ሰዎች ሁሉ በእርሱ መልክ የተፈጠሩ ከሆነ (ዘፍ. 1፥26-27) እግዚአብሔርም የወደቁትን ሰዎች ሁሉ ለመዋጀት ቃል ከገባ (ዘፍ. 3፥15)፣ እንግዲያውስ የእግዚአብሔር ፍቅር ለሰዎች ሁሉ መሆን ያለበት ትኩረት የእግዚአብሔር የመዋጀት ድርጊቶች ናቸው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

ቁጥሩ የሚገልጸው ያህዌ አሕዛብን መፍጠሩን በማስረገጥ ነው (ዘዳ. 32:8 LXX ላይ፣ እሱም ያህዌ ለእያንዳንዱ ሕዝብ ያህዌ ብሔራዊ መልአክ መስጠቱን ያስረግጣል፣ ዘዳ. 29:26፤ ዳንኤል 10)።

▣ **"ስምህንም ያከብራሉ"** አሕዛብ በእምነትና በአምልኮ ምላሽ በመስጠት የያህዌን ፍቅር እና መዋጀት ያከብራሉ (ኢሳ. 66፥23ሐ)።

መዝ. 86፥14-15 ዓመጸኞቹን አይሁድ የሚጠቅስ ከሆነ፣ በተቃራኒው የሚያምኑት አሕዛብ እጅግ ብርቱ ይሆናሉ!

***መዝሙር ፡ 86፥11-13***

**[11]አቤቱ፥ መንገድህን ምራኝ፥**
**በእውነትህም እሄዳለሁ**
**ስምህን ለመፍራት ልቤ ደስ ይለዋል።**
**[12]አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ በልቤ ሁሉ አመሰግንሃለሁ፥**
**ለዘላለምም ስምህን አከብራለሁ**
**[13]ምሕረትህ በእኔ ላይ ታላቅ ናትና፥**
**ነፍሴንም ከታችኛይቱ ሲኦል አድነሃታልና።**

**86፥11-13** ይህ አንጓ ያህዌን ይጣራል (ሁለት ተተኳሪዎች) ታማኝ ተከታዩ የሚያስፈልገውን እንዲሰጥ — መመሪያ እና አንድ የሆነ፣ ንጹሕ ልብ። በምላሹም ተከታዩ "ያስተምራል፣" "ይራመዳል፣" "ይፈራል፣" "ምስጋና ያቀርባል፣" እናም "ያከብራል" ያህዌን። ይህ የኪዳን ሥርዓት ነው፡ እግዚአብሔር ይሰጣል፣ ታማኝ ተከታዮችም ምላሽ ይሰጣሉ።

▣ ***"መንገድህ... እውነትህ... ስምህ"*** እነዚህ በግልጽ በትይዩ ዝምድና ናቸው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የሚሆነው

1. የየዕለቱ የሕይወት ስልት
2. የሚታወቅ እውነት
3. ፍጹም የሚታመን ሰው

እኔ ዘወትር የምለው ሰው (ኢየሱስ) ሊቀበል ይገባዋል (እንኳን ደኅና መጣህ ሊባል)፤ ስለዛ ሰው ያለ እውነትም ሊታመን ይገባዋል (መጽሐፍ ቅዱስ)፤ እንዲሁም የእዛን ሰውዬ የመሰለ ሕይወት ሊኖር! እነዚህ ሁሉ ይዘቶች ለተሟላ፣ ለተጠናቀቀ፣ እና ለመሰለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት አስፈላጊ ናቸው!

**86፡11- 12 "ልቤን አንድ አድርግልኝ... በልቤ ሁሉ"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ለአጠቃላይ ታማኝነትና መሰጠት (ማለትም፣ ኤር. 24:7፤ 32:39፤ ሕዝ. 11:33፤ 18:31፤ 36:26)።

**86፡12 "አመሰግንሃለሁ. . . አከብርሃለሁ"** እነዚህ ሁለት ግሦች ተጓዳኞች ናቸው።

1. ማመስገን – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ማክበር – ቢዲቢ 457፣ ኬቢ 455፣ ፒል ተጓዳኝ

▣የያህዌን ስም መጥራት (ማለትም፣ የእርሱን አካል፣ ባሕርይ) ወደ ዘፍ. 4:26 በመመለስ (ዘፍ. 12:8፤ 21:33፤ መዝ. 80:18፤ 145:1-2፤ ዳን. 9:19፤ ኢዩኤል 2:32፤ ሐዋ 2:21፤ ሮሜ. 10:9-13)። እነዚህ የእምነት፣ የአምልኮ፣ እና የምስጋና ድርጊቶች ናቸው። ታማኝ ተከታዮች ባደባባይ የማይታየውን የፍጥረትንና የመዋጀትን አምላክ ይጣራሉ። ልዩ ርዕስ ተመልከት መዝ. 86፡5 እና ልዩ ርዕስ፡ "ስሙ" የያህዌ።

▣ **"ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (ኦላም)።

**86፡13 "ነፍሴንም ከታችኛይቱ ሲኦል አድነሃታልና።"** ግሡ (ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717) ሂፊል የተጠናቀቀ ነው፣ እና ስለዚህ፣ እናም እንደ አለፈ፣ አሁን፣ ወይም የትንቢት ጊዜ ሊወሰድ ይችላል (ዐውደ-ጽሑፍ ብቻ ነው የሚወስነው)። ሲኦል የሙታን ማቆያ ስፍራ ነው። አይሁድ ተወዳጆቻቸውን ይቀብራሉ፣ ስለዚህ፣ እሱ በክስተታዊ (ሕሊናዊ) መልኩ እንደ ምድር መካከል ተደርጎ ይታይ ነበር። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው?

የመዝሙረኛውን ማጣቀሻ በበርካታ መንገዶች መረዳት ይቻላል።

1. ሕመም
2. የኪዳን ጠላቶች (ባልንጀራ አይሁድ)
3. የውጭ ጠላቶች (የአካባቢው ሕዝቦች)
4. መጻዒው የፍጻሜ ዘመን መልክ (የፍጻሜ ዘመን)

"ጥልቅ" የሚለው ቃል በጥሬው "ታችኛው" የሚል ቅጽል ነው (ቢዲቢ 1066፣ ዘዳ. 32:22)።

**መዝሙር ፡ 86፡14-17**

**[14]አቤቱ፥ ዓመፀኞች በእኔ ላይ ተነሥተዋል፥**
**የከፉዎችንም ማኅበር ነፍሴን ፈለጉአት**
**በፊታቸውም አላደረጉህም።**
**[15]አቤቱ፥ አንተ ግን መሐሪና ርኅሩኅ አምላክ ነህ**
**መዓትህ የራቀ ምሕረትህም እውነትህም የበዛ**
**[16]ወደ እኔ ተመልከት ማረኝም**
**ለባሪያህ ኃይልህን ስጥ፥**
**የሴት ባሪያህንም ልጅ አድን።**
**[17]ምልክትንም ለመልካም ከእኔ ጋር አድርግ**
**የሚጠሉኝ ይዩ ይፈሩም፥**
**አቤቱ፥ አንተ ረድተኸኛልና፥ አጽንተኸኛልምና።**

**86፡14** የእግዚአብሔር ታማኝ ተከታዮች ጠላቶች አሏቸው! እነዚህ እነማን እንደሆኑ ርግጠኝነት የለውም። ማንም ይሁኑ ማን እግዚአብሔርን አያውቁትም አልያም ለእግዚአብሔርም ሆነ ለእርሱ ሕዝብ እውቅና አይሰጡም (መዝ. 54፡3፣ ተመሳሳይ መዝ. 36፡1 ላይ)።

**86፡15** ማስታወሻ ተመልከት መዝሙር 86፡5 ላይ።

**86፡16** ይህ ትይዩ ነው ከመዝ. 86፡1 እና 3 ጋር።

▣ **"የሴት ባሪያህንም ልጅ አድን።"** ይህ ፈሊጥ ነው፣ ለጻድቅ ቤተሰብ፣ እግዚአብሔርን ለሚያገለግል (ማለትም፣ መዝ. 116፡16)።

**86፡17** ይህ ቁጥር የሚያመለክተው መዝ. 86፡14 ላይ ላሉት ልመና ነውን፣ ንስሐ እንዲገቡ፣ ወይስ ለሕዝብ ፍትሕ ጥሪ ነውን? መዝሙር 112፡10 ከዚህ ቁጥር ጋር ሊዛመድ ይችላል።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙረኛው ራሱን እንዴት ይገልጻል፣ መዝ. 86፡1-3 ላይ?
2. መዝ. 86፡8 እንዴት አድርጎ ከእስራኤል የተለየ አመለካከት፣ ይኸውም ከያህዌ አንድነት እና ብቻነት ጋር እንደሚገጥም አብራራ።
3. የመዝ. 86፡9ን ሁለንተናዊ (ዩኒቨርሳላዊ) አጽንዖት አብራራ።
4. በዚህ መዝሙር ጥቅም ላይ የዋሉትን የመለኮት ስሞች እና ሥነ-መለኮታዊ ጠቀሜታቸውን ዘርዝር።
5. አሀዳዊነትንና የእርሱን አንድምታ ከመዝ. 86፡5 እና 9 አኳያ ግለጽ።
6. የያህዌን ባሕርይ ዘርዝር፣ መዝ. 86:5፣ 10፣ 15 ላይ።

# መዝሙር 87

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጽዮን ዜጋ የመሆን ዕድል | የእግዚአብሔር ከተማ ክብር | ልጆች ጽዮንን ሲያመሰግኑ እንደ አማኞች እናት፣ በየስፍራው ላሉ | ኢየሩሳሌምን ማመስገን | ጽዮን የአሕዛብ እናት |
| ኤምቲ መግቢያ<br>የቆሬ ልጆች መዝሙር | | | | |
| 87:1-7 | 87:1-3 | 87:1-3 | 87:1-3 | 87:1-2 |
| | | | | 87:3 |
| | 87:4 | 87:4 | 87:4 | 87:4 |
| | 87:5-6 | 87:5-6 | 87:5-7 | 87:5 |
| | | | | 87:6-7 |
| | 87:7 | 87:7 | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር እግዚአብሔር ሕዝብን መምረጡን ያመሰግናል፣ እሱን እንዲገልጥና እንዲወክል፣ ለሌሎች አሕዛብ።

ለ. ጥቅም ላይ የዋለው ምስያ ከሕዝብ አንደኛው ነው (መዝ. 87፡4)። ያህዌ የሕዝቦችን ሁሉ ወሰኖችን አበጅቷል LXX፣ ዘዳ. 32:8፣ ማለትም፣ እሱ መልከዓ ምድርንና ታሪክን እየተቆጣጠረ ነው)።
የኪዳኑ ሕዝብ የተደራጀው
1. ከአብርሃም ዘሮች (ዘፍ. 12:1-3፤ ዘዳ. 7:6-8)
2. ከአባቶች ዘሮች (ይስሐቅ፣ ያዕቆብ/እስራኤል)
3. ከተለየ ምድር፣ ከነአን
4. ከተለየ ከተማ፣ ኢየሩሳሌም
5. ከተለየ ተራራ፣ ሞሪያ (ማለትም፣ መቅደስ፣ ዘዳ. 12:5፣11፣21፤ 14:23፣24፤ 16:2፣6፣11፣ etc.)

ሐ. ይህ የተለየ ሕዝብ (ዘጸ. 19፡5-6) ዓይነተኛ ነው፣ ሁሉንም ሕዝቦች ለመድረስ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

መ. ይሄንን መዝሙር ሳነብ ራሴን ጠየቅሁኝ፣ “ይህ አሁንም የእግዚአብሔር የተለየ ስፍራ ነውን?” በዚህ ላይ ታግያለሁ፤ እባክዎን ጊዜ ወስደው ልዩ ርዕሱን ያንብቡት፡ የብኪ የመጻኢው ትንቢቶች አልያም የአኪ ትንቢቶች። አኪ ሁለንተናዊ አድርጓቸዋል፣ የብኪን ትንቢቶች፣ ለዓለም። ወንጌል፣ እስራኤል ሳይሆን፣ የያህዌ ሙሉ መገለጥ ነው!

ሠ. መዝሙር 87፡4 የሚያመለክተው የፍጻሜ ዘመንን ነው፣ ሁሉም ሰዎች የእግዚአብሔር ሕዝብ አካል የሚሆኑበት (ማለትም፣ ኢሳ. 2:2-4፤ 12:4-5፤ 25:6-9፤ 42:6-12፤ 45:22-23፤ 49:5-6፤ 51:4-5፤ 60:1-3፤ 66:23)።

ረ. ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ 757፣ ተናጋሪው ማነው የሚለውን ጥያቄ ያነሣል፣ መዝ. 87፡4 እና 5 ላይ። እሱ የሚለውና እኔም የምስማማበት፣ መዝ. 87፡4 እግዚአብሔር መሆን አለበት (ምክንያቱም መለኮት በአንደኛ መደብ በመጠቀሱ፣ "እኔ")፣ መዝ. 87፡5 ደግሞ መዝሙረኛው ነው (ምክንያቱም መለኮት በሦስተኛ መደብ በመጠቀሱ፣ እንዲሁም መዝ. 87፡6)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 87፡1-7**

**1 መሠረቶቹ በተቀደሱ ተራሮች ናቸው**
**2 ከያዕቆብ ድንኳኖች ይልቅ፥**
**እግዚአብሔር የጽዮንን ደጆች ይወድዳቸዋል።**
**3 የእግዚአብሔር ከተማ ሆይ፥ ሴላህ**
**በአንቺ የተከበረ ነገር ይባላል።**
**4 የሚያውቁኝን ረዓብንና ባቢሎንን አስባቸዋለሁ**
**እነሆ፥ ፍልስጥኤማውያን ጢሮስም የኢትዮጵያም ሕዝብ፥**
**እነዚህ በዚያ ተወለዱ።**
**5 ሰው እናታችን ጽዮን ይላል፥ በውስጥዋም ሰው ተወለደ**
**እርሱ ራሱም ልዑል መሠረታት።**
**6 እግዚአብሔር ለሕዝቡ፥**
**በውስጥዋም ለተወለዱት አለቆችዋ በመጽሐፍ ይነግራቸዋል። ሴላህ**
**7 በአንቺ የሚኖሩ ሁሉ**
**ደስ እንደሚላቸው ይነግራቸዋል።**

**87፡1 "መሠረት"** ይህ የዕብራይስጥ ሥር (ቢዲቢ 414) በርካታ ፍችዎች አሉት።
1. የዕዝራ 7፡9 አጠቃቀም፣ እንደ አንድ ነገር መጀመሪያ
2. የከተማ መሠረት – መዝ. 137፡7፤ ሰቆ. 4፡11፤ ሚኪያስ 1፡6
3. መሠረትን ማኖር፣ በዘይቤአዊ መልኩ –ኢሳ. 28፡16
4. የምድር መፈጠር – 2 ሳሙ. 22፡16፤ መዝ. 18፡16፤ 78፡69፤ 82፡5፤ ኢሳ. 24፡18፤ 40፡21፤ ኤር. 31፡37
5. ከተራሮች ጋር የተያያዘ ምናባዊ ምስያ – ዘዳ. 32፡22፤ መዝ. 18፡7
6. መቅደሱ ከተመሠረተበት ጊዜ ጀምሮ – 2 ዜና. 8፡16 ወይም የእርሱ የጎን ክፍሎች – ሕዝ. 41፡8

▣ **"የተቀደሱ ተራሮች"** ተራሮች ተምሳሊትነታቸው
1. ቋሚነት
2. ጽናት
3. ወደ አምላክ ቅርበት (መዝ. 121፡1)
4. የምድር ምሰሶዎች

በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የእርሱ ምናባዊነት በግልጽ የሚያያዘው
1. ኢየሩሳሌም/ጽዮን (መዝ. 2፡6፤ 48፡1)
2. መቅደስ
3. የኪዳን ሕዝቦች

ብዙኀቱ ሊያያዝ የሚችለው ኢየሩሳሌም በሰባት ኮረብቶች ላይ መመሥረቷን ከሚያሳየው ሐቅ ጋር ነው። ለ"ጽዮን" ማስታወሻ ተመልከት በድረ-ገጽ መስመር፣ መዝ. 2፡6፤ 9፡11 እና 20፡2 ላይ።

ያህዌ ከበርካታ ተራራዎች ጋር ተያይዟል።
1. ሲና/ኮሬብ ተራራ (ዘጸአት 19-20)
2. ሲር/ፋራን ተራራ (ዘዳ. 33፡2፤ ዕን. 3፡3)
3. ሞሪያ ተራራ (ዘፍጥረት 22፤ሕዝ. 20፡40)
4. በሰሜን ያለ ተራራ (መዝ. 48፡2፤ ኢሳ. 14፡13፤ ሕዝ. 28፡14፣16)

**87፡2** ይህ ኢየሩሳሌምን/ጽዮንንና ይሁዳን ያመለክታል (መዝ. 78፡67-68)። ይሁዳ የመሲሑ ነገድ የሚሆነው ነው (ዘፍ. 49፡8-12)። "ያዕቆብ" ሁሉንም ነገዶች ያመለክታል፣ ከያዕቆብ/እስራኤል የሚወለዱትን። እሱም የወል ቃል ሆኖአል፣ ለኪዳን ሕዝቦች።

▣ **"እግዚአብሔር ይወድዳቸዋል"** ያህዌ ለኢየሩሳሌም ያለው ፍቅር ደግሞ ተለይቶ ተመልክቷል፣ መዝ. 78፡68 ላይ። እሱም የተመረጠው ስፍራው ነው (መዝ. 132፡13)።

▣ **"የእግዚአብሔር ከተማ"** ይህ ኢየሩሳሌምን ነው የሚያመለክተው (መዝ. 46፡4፤ 48፡8)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኢየሩሳሌም።

▣ **"ሴላህ"** ይህ ቃል የጽሑፋዊ ምድብ መዝጊያ ይመስላል፣ መዝ. 87፡6። ለተመለከቱት ፍችዎች የተሟላ ማስታወሻ መዝ. 3፡2 ተመልከት።

**87፡4 "እጠቅሳቸዋለሁ"** ይህን ግሥ (ቢዲቢ 289፣ ኬቢ 269፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ) መረዳት የሚቻለው እንደ "መመዝገብ" ነው (ቢዲቢ 271፣ ቁ. 4፣ እንደሚመዘግብ የሕዝብ ሠራተኛ መጠሪያ (2 ሳሙ. 8:16፤ 20:24፤ 1 ነገ. 4:3፤ 2 ነገ. 18:18፣37፤ 1 ዜና. 18:15፤ 2 ዜና. 34:8፤ኢሳ. 36:3፣ 22)፣ ብሎም እሱን የከተማ መመዝገቢያ ስፍራ ጋር የሚያያዝ ሐሳብ (መዝ. 87:5-6)።

▣ **"በሚያውቁኝ መካከል"** ይህ የሚያመለክተው በእነዚህ አገሮች ያሉ አሕዛብ የያህዌ አማኞችና ተከታዮች መሆናቸውን ነው። እነርሱ አሁን የአዲሲቱ የፍጻሜ ዘመን የእግዚአብሔር ከተማ ዜጎች ሆነዋል፣ "አዲሲቱ ኢየሩሳሌም" (ራዕይ 21)።

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ።

**87፡4-5** መዝሙረኛው በርካታ ሕዝቦችን ይዘረዝራል።

1. ራሃብ (ማለትም፣ ግብፅ፣ መዝ. 89:10፤ ኢሳ. 30:7)
2. ባቢሎን (አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ አሦር ለምን እንዳልተጠቀሰ፣ ምናልባት መዝሙሩ የተጻፈበትን ጊዜ አመላካች ሊሆን ይችላል)
3. ፍልስጥኤም
4. ጢሮስ (ማለትም፣ ፍንቄ)
5. ኢትዮጵያ (ማለትም፣ ኩሽ)

የእነርሱ መጠቀስ ዓላማ የእነርሱን መነሻ ለማነጻጸር ነው። አሕዛብ ሁሉ ከእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እንደ መጡ ለማሳየት (LXX፣ ዘዳ. 32:8)፣ እስራኤል ግን የእርሱ የተለየ ሕዝብ ነበር (ዘጸ. 19:5-6፤ ሮሜ. 9:4-5)።

**87፡5** የመዝ. 87፡5 የመጀመሪያው መስመር አስቸጋሪ ነው ነገር ግን ከዐውደ ጽሑፍ አኳያ፣ ማለትም ከመዝ. 87፡4 ሁለንተናዊ አጽንዖት፣ እሱ የሚያመለክተው በያህዌ የሚያምኑት ዜግነታቸው ወደ እግዚአብሔር ቅዱስ ከተማ— ጽዮን መዛወሩን ይመስለኛል።

**87፡6 "ተመዝግቧል"** ምናባዊ ምስያው የዜጎች ዝርዝር ነው፣ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ከተሞች የተቀመጠ። በተምሳሊታዊ መንገድ እስራኤል ከጽዮን መሆኑን የሚያሳይ ነው፣ የእግዚአብሔር ልዩ ከተማ፣ ያህዌን ለማምለክ የተለየ ስፍራ (መዝ. 87፡7)።

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሁለቱ የእግዚአብሔር መጻሕፍት።

**87፡7 "ይመነጫል"** ቃሉ (ቢዲቢ 745) በተምሳሊታዊ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፣ ለእግዚአብሔር ሕዝብ መገኛ ወይም መነሻ (ዘዳ. 33፡ 28)።

# መዝሙር 88
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ልመና ከሞት ለመዳን<br><br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>የቆሬ ልጆች መዝሙር ለመዘምራን አለቃ የይዝራኤላዊው የኤማን ትምህርት | የዕርዳታ ጩኸት | ልባዊ ጸሎት በሕመም ጊዜ ለፈውስ | የዕርዳታ ጩኸት | ጸሎት በታላቅ መከራ |
| 88:1-9 | 88:1-2 | 88:1-2 | 88:1-2 | 88:1-2 |
| | 88:3-7 | 88:3-7 | 88:3-7 | 88:3-5 |
| | | | | 88:6-7 |
| 88:10-12 | 88:8-9 | 88:8-12 | 88:8-9 | 88:8-9 |
| 88:13-18 | 88:10-12 | | 88:10-12 | 88:10-12 |
| | 88:13-18 | 88:13-18 | 88:13-18 | 88:13-16 |
| | | | | 88:17-18 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር ባሕርዩ
1. ተለጣጣቂ ጥያቄዎች፣ ከደራሲው በእግዚአብሔር የመተው ስሜት ጋር የተያያዘ፣ 88:10-12፤14። ይህ መዝሙር የሚያበቃው ያለ ምንም የሚታይ ተስፋ ወይም ዕረፍት ነው! ይህ "ጨለማው" መዝሙር ነው!
2. ተከታታይ መጠሪያዎች/ስሞች፣ ከዚህ ሕይወት በኋላ
   ሀ. ሲኦል፣ መዝ. 88:3ለ – ቢዲቢ 982፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: *ሲኦል*
   ለ. ጉድጓድ፣ መዝ. 88:4ሀ – ቢዲቢ 92 I
   ሐ. በሙታን መካከል፣ መዝ. 88:5ሀ – ቢዲቢ 559
   መ. በመቃብር የተኙት፣ መዝ. 88:5ለ — ቢዲቢ 868
   ሠ. ከእንግዲህ ወዲያ የማታስታውሳቸው፣ መዝ. 88:5ሐ
   ረ. ከእጅህ የተቆረጡ፣ መዝ. 88:5መ፣ ሰቆ. 3:54
   ሰ. ታችኛው ጉድጓድ፣ መዝ. 88:6ሀ – ቢዲቢ 1066
   ሸ. ጨለማ ስፍራዎች፣ መዝ. 88:6ለ – ቢዲቢ 365
   ቀ. ጥልቆች፣ መዝ. 88:6ለ – ቢዲቢ 846 (ሰ፣ ሸ፣ ቀ ትይዩ ናቸው)
   በ. ሙታን፣ መዝ. 88:10ሀ – ቢዲቢ 559
   ተ. ተስፋ የቆረጡ መንፈሶች፣ መዝ. 88:10ለ – ቢዲቢ 952 I
   ቸ. መቃብር፣ መዝ. 88:11ሀ – ቢዲቢ 868
   ኀ. የጥፋት ስፍራ፣ መዝ. 88:11ለ – አባዶን – ቢዲቢ 2
   ነ. ጨለማው፣ መዝ. 88:12ሀ – ቢዲቢ 365፣ 1 ሳሙ. 2:9፤ ኢዮብ 10:21፤ 17:13፤ 18:18
   ኘ. የመረሳት ምድር፣መዝ. 88:12ለ – ቢዲቢ 75 አወቃቀር ቢዲቢ 674 (በዚህ መዝሙር ላይ ያልተለመደ፣ መዝ. 6:5)

ኢ. ጨለማ፣ መዝ. 88:18ለ – ቢዲቢ 365

ለ. የእግዚአብሔርን አለመቀበል ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን የተለያዩ ቃላት ተገንዘብ።
1. ቍጣህ፣መዝ. 88:7ሀ – ቢዲቢ 404
2. ሞገድህ፣ መዝ. 88:7ለ – ቢዲቢ 991፣ መዝ. 42:7፤ 69:1፣14-15፤ ዮናስ 2:3
3. ናቅሃቸው፣ መዝ. 88:14ሀ – ግሥ፣ ቢዲቢ 276 I፣ ኬቢ. 276፣ ቃል ያልተጠናቀቀ
4. ፊትህን ሰወርከ፣ መዝ. 88:14ለ – ግሥ፣ ቢዲቢ 711፣ ኬቢ 771፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ
5. ድንጋጤዎችህ፣ መዝ. 88:15ለ – ቢዲቢ 33
6. የሚነድ ቍጣህ፣ መዝ. 88:16ሀ – ቢዲቢ 354
7. ድንጋጤዎችህ፣ መዝ. 88:16ለ – ቢዲቢ 130 (እዚህና ኢዮብ 6:4 ላይ ብቻ)

ሐ. ከዚህ አጭር መዝሙር አኳያ ለማወቅ አዳጋች ነው፣ መዝሙረኛው
1. ታምሞ ከሆነ (ለምጽ ሊሆን ይችላል፣ በቤተሰቡና በጓደኞቹ በመተዉ ምክንያት)
2. ከፍርድ የተነሣ መከራ የሚቀበል
3. ብቸኛ የመሆን ስሜት አድሮበት እንደሁ
4. ከሕይወት ሁኔታዎች የፈራ ሊሆን ይችላል

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 88፡1-9**

**1 አቤቱ፥ የመድኃኒቴ አምላክ፥**
**በቀንና በሌሊት በፊትህ ጮኽሁ**
**2 ጸሎቴ ወደ ፊትህ ትግባ፥**
**ጆሮህንም ወደ ጩኸቴ አዘንብል**
**3 ነፍሴ መከራን ጠግባለችና፥**
**ሕይወቴም ወደ ሲኦል ቀርባለችና።**
**4 ወደ ጓድጓድ ከሚወርዱ ጋር ተቈጠርሁ፥**
**ረዳትም እንደሌለው ሰው ሆንሁ።**
**5 ለዘላለም እንደማታስባቸው፥**
**እንደ ተገደሉና በመቃብር ውስጥ እንደ ተጣሉ፥**
**በሙታን ውስጥ እንዳሉ የተጣልሁ ሆንሁ**
**እነርሱም ከእጅህ ተለዩ።**
**6 በጨለማና በሞት ጥላ ውስጥ፥**
**በታችኛው ጕድጓድ አስቀመጥኸኝ።**
**7 በእኔ ላይ ቍጣህ ጸና፥**
**መቅሠፍትህን ሁሉ በእኔ ላይ አመጣህ። ሴላህ**
**8 የሚያውቁኝን ከእኔ አራቅህ**
**በእነርሱ ዘንድ ርኩስ አደረግኸኝ**
**ያዞኝ፥ መውጫም የለኝም።**
**9 ዓይኖቼም በመከራ ፈዘዙ**
**አቤቱ፥ ሁልጊዜ ወደ አንተ ጮኽሁ፥**
**እጆቼንም ወደ አንተ ዘረጋሁ፥**

**88፡1 "አቤቱ አምላክ"** ይህ መዝሙር ለመለኮት የኪዳን ስምን ይጠቀማል፣ ያህዌ፣ በስም ጠሪ አመልካችነት መልኩ፣ ሦስት ጊዜ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ **"የመድኃኒቴ አምላክ"** ይህ የመለኮት መጠሪያ (መዝ. 24:5፤ 27:9) መዝሙረኛው፣ ያህዌ ምን እንዲያደርግለት የሚፈልገውን መግለጫ ነው፣ "እንዲያድን፣" "እንዲታደግ፣" "በእርሱ አኳያ እንዲያደርግ።" ይህ የመከፈቻ ቁጥር እጅግ "አዎንታዊው" የመዝሙሩ ስንኝ ነው። ያህዌ የኪዳን አምላክ ነው፣ መዝሙረኛውም ይጸልያል ነገር ግን ምንም ምላሽ እንዳገኘ አይሰማውም። እሱ እንዲያውም እግዚአብሔር ሆን ብሎ ችግሩን እንዳመጣበት ይሰማዋል!

▣ **"እኔ"** የአንደኛ መደብ ነጠላ ተውላጠ ስሞችንና ሁለተኛ መደብ ነጠላ ተውላጠ ስሞች ብዛትን ("አንተ") ተገንዘብ። ይህ እጅግ ግላዊ ጩኸት ነው፣ ከአማኝ ወደ አምላኩ።

▣ **"ጮኽሁ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 858፣ ኬቢ 1042) ከብዙዎቹ የተጠናቀቁ ግሦች ቀዳሚው ነው። መዝሙረኛው በጽናት እግዚአብሔርን መፈለጉን አስረግጧል፣ እግዚአብሔር ግን ገና ምላሽ አልሰጠም (መዝ. 88:13-18)።

▣ **"በቀንና በሌሊት"** ይህ ሐረግ የመዝሙረኛው ቋሚ ጸሎት ማስረገጫ መንገድ ነው (መዝ. 22:2፤ 25:5፤ 86:3)።

**88፡2** ይህ ቁጥር ሁለት ትይዩ ጥያቄዎች አሉት።
1. ጸሎቴ ወደ ፊትህ ትግባ – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ (መዝ. 18:6)፤ መዝሙረኛው ጸሎቱ ገና የተሰማ አልመሰለውም (መዝ. 88:9፣13፣14)
2. ጆሮህንም ወደ ጩኸቴ አዘንብል – ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ *ሂፊል ተተኳሪ* (መዝ. 17:6፤ 31:2፤ 71:2፤ 86:1፤ 102:2)

**88፡3-9** መዝሙረኛው ምክንያቶቹን ይዘረዝራል፣ እግዚአብሔር ለምን መስማትና ምላሽ መስጠት እንደሚኖርበት (የተጠናቀቀው ጊዜ (ግሥ) የጸናውን ሁኔታ ይገልጻል)።
1. ነፍሱ (ቢዲቢ 659) ተሞልታለች (ሌላ የተጠናቀቀ) በችግሮች፣ መዝ. 88፡3ሀ
2. ሕይወቱ (ቢዲቢ 313) ደርሳለች (ሌላ የተጠናቀቀ) ወደ ሲኦል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው?)፣ መዝ. 88፡3ለ
3. እሱ ተቆጥሯል (ሌላ የተጠናቀቀ) ወደ ጉድጓድ ከሚወርዱ ጋር (መዝ. 28:1፤ 143:7)፣ መዝ. 88፡4ሀ
4. እሱ ሆኗል (ሌላ የተጠናቀቀ) ኃይል እንደሌለው ሰው (ማለትም፣ ረዳት-አልባ፣ ቢዲቢ 33፣ እዚህጋ ብቻ ብኪ ላይ፤ አራምኛ የብድር ቃል)፣ መዝ. 88፡4ለ
5. እሱ ተትቷል "በሙታን መካከል"፤ ቅጽሉ የተተረጎመው "መተው" በሚል ነው "ልቅ መደረግ፣" ቢዲቢ 344፣ መዝ. 88፡5ሀ
   አኪጀት "መዋለል"
   አእት፣ ጀፒኤስኦኤ "መተው"
   አኢመቅ "ብቻን መተው"
   ኤምቲ "ልቅ መደረግ" የሚል አለው፣ እናም ከሕይወት ኃላፊነቶች ነጻ መሆንን የሚያመለክት ይመስላል (ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት፣ ገጽ 350)።
6. ዳግመኛ እንደማታስታውሰው (ሌላ የተጠናቀቀ)፣ መዝ. 88፡5ሐ
7. ከአንተ የተለየ (ሌላ የተጠናቀቀ) ከእጅህ፣ መዝ. 88፡5መ
8. አንተ ያስቀመጥከው (ሌላ የተጠናቀቀ) ከዝቅተኛው ጉድጓድ፣ መዝ. 88፡6ሀ
9. አንተ በጨለማ ስፍራ ያኖርከው፣ በታችኛው ጉድጓድ፣ መዝ. 88፡6ለ
10. ያንተ ቍጣ ያረፈበት ("ክብደት ያረፈበት፣" ሌላ የተጠናቀቀ) መዝ 88፡7ሀ ይህ ግሥ ቢዲቢ 701፣ ኬቢ 759 በአብዛኛው ጥቅም ላይ የሚውለው ያህዌ አንዱን ሲደግፍ ነው፣ እዚህ ግን፣ በተቃራኒው ነው)
11. መከራን ያሳየኸው ("በችግር መዋጥ" ሌላው የተጠናቀቀ) በመቅሠፍትህ ሁሉ፣ መዝ. 88፡7ለ
12. የሚያውቁትን ሁሉ ከእርሱ አራቅህ (ሌላ የተጠናቀቀ)፣ መዝ. 88፡8ሀ
13. የመጸየፍ ማሳያ ያደረግከው (ሌላ የተጠናቀቀ)፣ መዝ. 88፡8ለ
14. የዘጋህበት፣ መዝ. 88፡8ሐ
15. ዓይኖቹ ፈዘዙ (ሌላ የተጠናቀቀ)፣ መዝ. 88፡9ሀ
16. በየቀኑ ይጠራሃል (ሌላ የተጠናቀቀ)፣ መዝ. 88፡1ለ፣9ለ
17. እጆቹን ዘርግቷል (ማለትም፣ ጸሎት፣ ሌላ የተጠናቀቀ) ወዳንተ፣ መዝ. 88፡9ሐ

ቅንብሮቹን ተመልከት
1. የመዝሙረኛው ድርጊቶች
2. እሱ የሚያስረግጣቸው ነገሮች፣ እግዚአብሔር እንዳደረገለት

**88፡7 "ሴላህ"** መዝሙር 3፡2 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**88፡8 "የሚያውቁኝ"** ይህ (ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390) *ፖል* አንቀጽ ነው "ማወቅ" ከሚለው ግሥ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ)። ተመሳሳይ ዓይነት መዝ. 88፡18 ላይ አብሮ አለ
1. ፍቅረኛ – ቢዲቢ 12፣ ኬቢ 17 *ቃል* አንቀጽ
2. ወዳጅ – ቢዲቢ 945

ይህ ሰው ባጠቃላይ ከእግዚአብሔርና ከሌሎች ሰዎች እንደተነጠለ ተሰምቶታል!

**88፡9** መዝሙር 88:9 ከመዝ. 88:1 ጋር ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ተመሳሳይ ነው፣ እና ምናልባት የአካታች ምሳሌ ሊሆን ይችላል።

## መዝሙር ፡ 88፡10-12

**10 በውኑ ለሙታን ተአምራት ታደርጋለህን?**
**የሞቱትስ ተነሥተው ያመሰግኑሃልን?**
**11 በመቃብርስ ውስጥ ቸርነትህን፥**
**እውነትህንስ በጥፋት ስፍራ ይናገራሉን?**
**12 ተአምራትህ በጨለማ፥**
**ጽድቅህንም በመርሳት ምድር ትታወቃለችን?**

**88፡10-12** ይህ አንጓ የሚገልጸው አጠቃላዩን የብኪ እይታ ነው፣ ደስታ-የለሽ፣ ጸጥ ያለ ሕላዌ፣ ንቁ ነፍስ/አካል/እኔነት ከሞት በኋላ።
1. እግዚአብሔር አይታደግም ("ማዳን") ከሞት
2. ሙታን እግዚአብሔርን አያመሰግኑም (መዝ. 6:5፤ 30:9፤ 115:17፤ ኢሳ . 38:18)
3. የእግዚአብሔር ታማኝነት በመቃብር አይነገርም (ኢሳ. 38:18)

4. የእግዚአብሔር የማዳን ሥራ (ቢዲቢ 810፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ድንቅ ነገሮች) በጨለማ ስፍራ አይነገሩም
5. የእግዚአብሔር ጽድቅ (ማለትም፣ የማዳን ሥራው) በመርሳት ምድር አይታወቅም

**88:10**
**አአመመቅ** **"የተለዩ ነፍሶች"**
**አኪጀት፣ አእቅ** **"ሙታን"**
**አየተመቅ፣ ጀፒኤስአኤ፣**
**የተእመቅ** **"ጥላዎች"**
**አኢመቅ** **"ጥላዎች"**

ይህ የዕብራይስጥ ሥር (ቢዲቢ 952) ሁለት ፍችዎች/አጠቃቀሞች አሉት።
1. የግዙፋን ዘር (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ለረዣዥም/ኃይለኛ ተዋጊዎች ወይም የሕዝብ ወገኖች መጠሪያነት ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት) – ዘፍ. 14:5፤ 15:20፤ ዘዳ. 2:20፤ 3:11፤ ኢያ. 17:15፤ 1 ዜና. 20:4
2. የተለዩት/ንቁ ሙታን – ኢዮብ 26:5-6፤ ምሳ. 2:18፤ 9:18፤ 21:16፤ ኢሳ. 14:9፤ 26:11-19፤ ይህ አጠቃቀም በጥበብ ሥነ-ጽሑፍ የተለመደ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ)

ከኢሳይያስ 14 እና ሕዝቅኤል 28 የተነሣ እነዚህን እንደ ተለዩ ነገሥታት እና ብርቱ ሰዎች መመልከት ይቻላል፣ አሁን በሲኦል ያሉ፣ ኃይላቸውና ብልጽግናቸው ሄዷል። የዚህ ቃል ዝርዝር ማብራሪያ አለ፣ ኒዶቴ ቅጽ 3 ገጽ 1173-1180 ላይ።

▣ **"ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት ፣ መዝ. 3፡2 ላይ።

## መዝሙር ፡ 88፡13-18

**[13]አቤቱ፥ እኔ ግን ወደ አንተ ጮኽሁ**
**በጥዋት ጸሎቴ ወደ ፊትህ ትደርሳለች።**
**[14]አቤቱ፥ ነፍሴን ለምን ትጥላለህ?**
**ፊትህንስ ከእኔ ለምን ትሰውራለህ?**
**[15]እኔ ከታናሽነቴ ችግረኛ ለሞትም የቀረብሁ ነኝ**
**ከፍ ከፍ ካልሁ በኋላ ግን ተዋረድሁ ተናቅሁም።**
**[16]መቅሠፍትህ በላዬ አለፈ፥**
**ግርማህም አስደነገጠኝ።**
**[17]ሁልጊዜ እንደ ውኃ ከበቡኝ፥**
**በአንድነትም ያዙኝ።**
**[18]ወዳጀንና ባልንጀራዬን ዘመዶቼንም**
**ከመከራ የተነሣ ከእኔ አራቅህ።**

**88፡13-18** ይህ ቀደም ብለው የነበሩትን ቁጥሮች አጽንዖት ይደግማል። መዝሙረኛው ከእግዚአብሔር እና ከቤተሰብ እና ከወዳጆቹ የተገለለ ይመስለዋል! ብቸኛ ነው! ይህ መዝሙር በተስፋ መቁረጥ ያበቃል (መዝ. 88:14)! እሱም ሊገባው አልቻለም፣ በእርሱ ላይ የሚሆንበት፣ በሥጋዊም ሆነ መንፈሳዊ!

**88፡15** ይህ መዝሙር የሚያመለክተው መዝሙረኛው ከወጣትነቱ ጀምሮ እንደታመመ እና ወደ ሞት እንደተቃረበ ነውን ወይስ ይህ በእግዚአብሔር የመተው የተራዘመ ምናባዊ ስሜት ነውን?

ኤምቲ ላይ ያለው ግሥ (ቢዲቢ 806፣ ኬቢ 918፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) ከሁለት የአንዱ ሥሮች ሊሆን ይችላል።
1. הנופא – ቢዲቢ 67፣ ወይም (1) "ረዳት አልባነት፣" (2) "ግራ መጋባት፣" ወይም (3) "በጣም እጅግ የበዛ"
2. פון – እዚህጋ ብቻ የሚገኝ፣ ፍችውም ርግጠኛ ያልሆነ
3. גופ – "በስሜት አልባነት ማደግ" (አእት መጽሐፍ ቅዱስ)

ይህ ቁጥር ለመተርጎም አስቸጋሪ ነው፣ ኤምቲ አስቸጋሪ በመሆኑ ሳቢያ (ጀፒኤስአኤ የግርጌ ማስታወሻ)
LXX "ከፍ ካልኩኝ በኋላ፣
ተዋረድኩኝ፣ ግራ የተጋባሁም ሆንኩኝ"
ፔሺታ "ኩሩ ነበርኩኝ፣ አሁን ግን ተዋረድኩ ደቀቅኩም"

**88፡18 "በጨለማ"** ተመሳሳይ ተናባቢዎች ሊሆኑ የሚችሉት "መያዝ" (ፔሺታ)። ጀፒኤስአኤ የኤምቲን "ጨለማ" ወስዶ "ማየት የማይችል" በሚል ይተረጉመዋል።

# የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይሄንን መዝሙር ስታነብ የመጀመሪያ ምልከታህ ምንድነው?
2. የመዝሙረኛው ችግር ምንድነው?
3. እግዚአብሔር እንደተወው ለምን ሊሰማው ቻለ? አንዳች ተስፋ ገልጿልን? እንዴት?
4. የብኪን የከሞት በኋላን አተያይ ግለጽ።
5. መዝ. 88፡4 እጅግ የሚያሳምመው ለምንድነው?
6. መዝሙረኛው አንዳች ተስፋ ገልጿልን፣ እግዚአብሔር እንደሚሰማ፣ እንደሚመጣ፣ እንደሚረዳ?

# መዝሙር 89
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጌታ ኪዳን ከዳዊትና ከእስራኤል መከራ<br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>የይዝራኤላዊው የኤማን ትምህርት | ከዳዊት ጋር የተደረገውን ኪዳን ማስታወስና፣ ስለ ጠፋው ባርኮት ማዘን | የንጉሥ ጸሎት ከጠላቶቹ ለመታደግ | ዝማሬ በብሔራዊ ችግር ሰዓት | ውዳሴና ጸሎት ለታማኙ አምላክ |
| 89:1-4 | | | | |
| | 89:1-2 | 89:1-2 | 89:1-4 | 89:1-2 |
| | 89:3-4 | 89:3-4 | | 89:3-4 |
| 89:5-10 | | | | |
| | 89:5-10 | 89:5-18 | 89:5-14 | 89:5-6 |
| | | | | 89:7-8 |
| | | | | 89:9-10 |
| 89:11-18 | | | | |
| | 89:11-18 | | | 89:11-12 |
| | | | | 89:13-14 |
| | | | 89:15-18 | 89:15-16 |
| | | | የአምላክ ተስፋ ለዳዊት | 89:17-18 |
| 89:19-29 | | | | |
| | 89:19-23 | 89:19-37 | 89:19-29 | 89:19 |
| | | | | 89:20-21 |
| | | | | 89:22-23 |
| | 89:24-29 | | | 89:24-25 |
| | | | | 89:26-27 |
| | | | | 89:28-29 |
| 89:30-37 | | | | |
| | 89:30-37 | | 89:30-34 | 89:30-31 |
| | | | | 89:32-33 |
| | | | 89:35-37 | 89:34-35 |
| | | | ሰቆቃ በንጉሥ መሸነፍ | 89:36-37 |
| 89:38-45 | | | | |
| | 89:38-45 | 89:38-45 | 89:38-45 | 89:38-39 |
| | | | | 89:40-41 |
| | | | | 89:42-43 |
| | | | | 89:44-45 |
| 89:46-48 | | | | |
| | 89:46-48 | 89:46-48 | 89:46-48 | 89:46-48 |
| 89:49-51 | | | | |
| | 89:49-51 | 89:49-51 | 89:49-51 | 89:49-51 |
| 89:52 | | | | |
| | 89:52 | 89:52 | 89:52 | 89:52 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የሚያስረግጠው የያህዌን ቋሚ ምርጫ ነው፣ አብርሃምንና ቤተሰቡን፣ በኪዳናዊ ተስፋ (ዘፍ. 12:1-3፤ 15:12-21)። እነዚህ የኪዳን ተስፋዎች ሙሉ ለሙሉ ሆነዋል፣ በዳዊትና በእርሱ ይሁዳዊ ዘር ንግሥና (2 ሳሙኤል 7፡ 1 ነገ. 8፡16)።

ለ. ያህዌ የሕዝቡ ፈጣሪና መጋቢ ነው (መዝ. 89፡11-18)። እሱ የሰማያዊው ጉባኤ መሪ ነው (መዝ. 89፡5-10፣19)፣ ይኸውም የእርሱን ዓላማ ለመፈጸም የሚኖር።

ሐ. ነገር ግን አሳዛኝ ነገር ሆኗል፡ የእርሱ ሕዝብና መሪዎቻቸው ታማኞች አልሆኑም፣ ታዛዦች አልሆኑም (መዝ. 89፡38-45)። እንግዲህ ችግር አለ።

1. እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቷል
2. ሕዝቡም አልሆነላቸውም

እሱ ምን ያደርጋል (መዝ. 89:46-48፣49-51)?

መ. አስደናቂ የሚሆነው ይህ መዝሙር፣ ከአብዛኞቹ መዝሙራት በተለየ፣ በኢየሩሳሌም ላይ አያተኩርም (ነገር ግን መዝ. 89፡1-2፣5 የሚያመለክተው የመቅደስ አምልኮን ነው) እና ቤተ መቅደስ፣ ነገር ግን ዳዊታዊ ዘር ላይ ነው። እሱ በርግጥ ከ2 ሳሙኤል 7 የመጣ ነው፣ ይኸውም ስለ ሁለቱ የሆነ

1. የቤተ መቅደሱ መገንባት
2. የዳዊት ሥርወ-መንግሥት መቀጠል

ቁጥር 1 በዚህ መዝሙር ላይ ተለይቶ እንኳን አልተጠቀሰም።

ሠ. ማስታወሻ ለማሳየት ያህል፣ አኪ እነዚህን የብኪ የእስራኤል ተስፋዎች እንዴት እንደሚተረጉማቸው። እባክዎትን የእኔን ኮሜንተሪ ይመልከቱ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር (www.freebiblecommentary.org) ሮሜ 2:28-29፤ 9:6፤ ገላ. 3:7-9፣26፤ 6:16፤ 1 ጴጥ. 3:6 ላይ! አኪ የእግዚአብሔርን ተስፋዎች ያሰፋቸዋል፣ የአዳም ልጆችን ለማካተት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

ረ. በሥነ-መለኮታዊ ክርክሮች ላይ፣ ሁኔታዊ በሆነ እና ሁኔታዊ ባልሆነ የኪዳን ተስፋዎች፣ ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 89፡30-37 ላይ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 89፡1-4**

**[1]አቤቱ፥ ምሕረትህን ለዘላለም እዘምራለሁ፥**
**እውነትህንም በአፌ ለልጅ ልጅ እናገራለሁ።**
**[2]እንዲህ ብለሃልና። ምሕረት ለዘላለም ይመሠረታል፥**
**እውነትህም በሰማይ ይጸናል።**
**[3]ከመረጥሁት ጋር ቃል ኪዳኔን አደረግሁ፥**
**ለባሪያዬም ለዳዊት ማልሁ።**
**[4]ዘርህን ለዘላለም አዘጋጃለሁ፥**
**ዙፋንህንም ለልጅ ልጅ እመሠርታለሁ። ሴላህ።**

**89፡1-4** ይህ አንጓ አአመመቅ ላይ ወደ ሁለት አንጓዎች ይከፈላል (መዝ. 89፡1-2፣ 3-4) አኪጀት፣ አየተመቅ፣ አኢመቅ ላይ ሁለት ተናጋሪዎች በመኖራቸው ሳቢያ።

1. መዝሙረኛው መዝ. 89፡1-2
   ሀ. እዘምራለሁ – ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ *ቃል ተጓዳኝ*
   ለ. አስታውቃለሁ – ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   ሐ. ብያለሁ. . . – ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
2. ያህዌ ራሱ መዝ. 89:3-4 ላይ
   ሀ. ኪዳንን አድርጌአለሁ – ቢዲቢ 503፣ ኬቢ 500፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
   ለ. ቃል ገብቻለሁ – ቢዲቢ 989፣ ኬቢ 1396፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ
   ሐ. እመሠርታለሁ – ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 464፣ *ሂፊል* IMየተጠናቀቀ
   መ. እገነባለሁ – ቢዲቢ 124፣ ኬቢ 139፣ *ቃል* የተጠናቀቀ ከዋው ጋር (ከተጠናቀቁት ጋር ይያያዛል፣ ሀ እና ለ ላይ)

**89፡1** ሦስት ቃላት አሉ በዚህ መዝሙር ላይ በርካታ ጊዜ የሚከሰቱ።

1. ቸርነት፣ መዝ. 89፡1፣2፣14፣24፣28፣33፣49 – ልዩ ርዕስ ተመልከት: ቸርነት (*ሄሴድ*)
2. ዘላለም፣ መዝs. 89፡1፣2፣4፣28፣37፣52 – ልዩ ርዕስ ተመልከት: ዘላለም (*ኦላም*)
3. ታማኝነት፣ መዝ. 89፡1፣2፣5፣8፣24፣33፣49 – ልዩ ርዕስ ተመልከት: ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ

እነርሱ የእስራኤልን ተስፋ የመሠረቱት በእግዚአብሔር ጥሪ፣ ጸጋ፣ ጥበቃ፣ እና መጋቢነት ላይ ነው፣ ለዘላለም።

"ዘላለም" የሚለው ቃል "ሁሉም ትውልድ" ከሚለው ጋር ትይዩ ነው (መዝ. 89፡1ለ፣ 4ለ)።

**89፡3 "ኪዳን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን።

▣ **"የመረጥኩት... ዳዊት"** ይህ ሊያመለክት የሚችለው
1. የዳዊት በንጉሥነት መመረጥ፣ በሳኦል ላይ፣ 1 ሳሙኤል 16፤ 2 ሳሙ. 7፡8
2. የዳዊት ተስፋ ስለ ዝርዮቹ፣ 2 ሳሙ. 7፡12-17

▣ **"ባሪያዬ"** ይህ የክብር መጠሪያ ሆኗል (አንዳንድ ምሳሌዎች)።
1. ሙሴ – ዘኍ. 12:7፤ ኢያ. 1:2
2. ኢያሱ – መሳ. 2:8
3. ዳዊት – 1 ነገ. 8:24፣25፣26፤ መዝ. 89:20
4. ሰሎሞን – 1 ነገ. 8:28
5. መሲሕ – ኢሳ. 42:1፤ 52:13-53:12
6. እስራኤል – ኢሳ. 41:8፤ 42:19፤ 43:10፤ 44:1፣21

**89፡4** ይህ የ2 ሳሙኤል 7 ጠቃሽ ነው። ይህ መዝሙር በርካታ ጠቃሾች አሉት፣ ያህዌ ለዳዊትና ለዘሩ የሰጠው ተስፋ።
1. መዝ. 89:4 – 2 ሳሙ. 7:13፣16
2. መዝ. 89:22 – 2 ሳሙ. 7:10
3. መዝ. 89:23 – 2 ሳሙ. 7:9
4. መዝ. 89:29 – 2 ሳሙ. 7:13፣16
5. መዝ. 89:33 – 2 ሳሙ. 7:15
6. መዝ. 89:35 – 2 ሳሙ. 7:8-17

▣ **"ዙፋንህ ለልጅ ልጅ ነው"** ይኸው ተመሳሳይ ተስፋ ተደርጓል፣ ኢሳ. 9:7፤ ዳን. 2:44፤ 7:14፣18፣27፤ ሉቃስ 1:33። ያህዌ ዘላለማዊ የማዳን ዕቅድ አለው፣ ለሰዎች ሁሉ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።
"ትውልዶች" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ የዋለው
1. ለኖኅ ተስፋ – ዘፍ. 9:12
2. ለአብርሃም ተስፋ – ዘፍ. 17:7፣9
3. ለእስራኤል ተስፋ – ዘዳ. 7:9
4. ለዳዊት ተስፋ – መዝ. 89:4 (2 ሳሙ. 7:13፣16ን ያንጸባርቃል)

▣ **"ሴላህ"** ይህ መዝ. 89:4፤ 37፣ 45፣ 48 ላይ ይከሰታል። እሱም ዘወትር የሚያገለግለው አንጓን ለመዝጊያ ነው። ስለ ቃሉ ትርጉም (ቢዲቢ 699) ማስታወሻ ተመልከት፣ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር መዝ. 3:2 ላይ።

**መዝሙር ፡ 89፡5-10**

**5አቤቱ፥ ሰማያት ተኣምራትህን**
**እውነትህንም ደግሞ በቅዱሳን ማኅበር ያመሰግናሉ።**
**6እግዚአብሔርን በሰማይ የሚተካከለው ማን ነው?**
**ከአማልክትስ ልጆች እግዚአብሔርን ማን ይመስለዋል?**
**7በቅዱሳን ምክር እግዚአብሔር ክቡር ነው**
**በዙሪያው ባሉት ሁሉ ላይ ታላቅና ግሩም ነው።**
**8አቤቱ የሠራዊት አምላክ፥ እንደ አንተ ያለ ማን ነው?**
**አቤቱ፥ አንተ ብርቱ ነህ፥ እውነትህም ይከብብሃል።**
**9የባሕርን ኃይል አንተ ትገዛለህ፥**
**የሞገዱንም መናወጥ አንተ ዝም ታሰኘዋለህ።**
**10አንተ ረዓብን እንደ ተገደለ አዋረድኸው፥**
**በኃይልህም ክንድ ጠላቶችህን በተንሃቸው።**

**89፡5-10** ይህ አንጓ ሁለት ጭብጦች አሉት።
1. ያህዌ የመልአካዊው ጉባኤ መሪ መሆኑ (መዝ. 89፡5-8)
   ሀ. ሰማያት — ለመልአካዊው ጉባኤ ሰውኛ (ዘይቤ) የሆነ፣ መዝ. 89፡5ሀ
   ለ. የቅዱሳን ጉባኤ፣ መዝ. 89፡5ለ – ቢዲቢ 874 አወቃቀር ቢዲቢ 872
   ሐ. የአማልክት ልጆች፣ መዝ. 89፡6 – ቢዲቢ 119 አወቃቀር ቢዲቢ 42፣ ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 29:1 እና 82:1 ላይ
   መ. የቅዱሳን ጉባኤ፣ መዝ. 89፡7ሀ – ቢዲቢ 691 አወቃቀር ቢዲቢ 872
   ሠ. በእርሱ ዙሪያ ያሉት ሁሉ፣ መዝ. 89፡7ለ
   ረ. ለተሻለ የዕብራይስጥ ቃላት ማብራሪያ፣ ሚላርድ ኢሪክሰን፣ *ክርስቲያን ሥነ-መለኮት*፣ 2ኛ ዕትም፣ ገጽ 412 ተመልከት
2. ያህዌ እንደ ፈጣሪ (ማለትም፣ በውኃው መናወጥ ላይ) እና የእስራኤል ቅዱስ ተዋጊ (ማለትም፣ በግብፅና በከነአን ላይ፣ መዝ. 89፡9-10)

ሁለት ልዩ ርዕሶች አሉ "ልጅ" የሚለውን ቃል አጠቃቀም ግልጽ ለማድረግ የሚረዱ
1. ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር ልጅ

2. ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር ልጆች (ዘፍጥረት 6)
ደግሞም ግሩም የሆነውን ጽሑፍ ተመልከት ኒዶቴ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 671-677፣ በተለይም 676 ላይ።

**89፡5 "ሰማያት"** ይህ አንድም

1. ሰውኛ ዘይቤ ነው
   ሀ. የመሬት
   ለ. የእግዚአብሔር ማደሪያ ("በሰማያት ያለ" ከሚለው ጋር ትይዩ የሆነ)
2. ሌለኛው መንገድ፣ መልአካዊውን ጉባኤ ለመጥቀስ (ከላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)

▣ **"አቤቱ ጌታ"** በዚህ አንጓ ላይ ያሉትን የመለኮት ስሞች/መጠሪያዎች ተገንዘብ።

1. ጌታ፣ መዝ. 89:2፣ 5፣ 6 (ሁለቴ)፣ 8 – ያህዌ
2. እግዚአብሔር፣ መዝ. 89:7 – ኤል
3. የሠራዊት አምላክ ፣ መዝ. 89:8 – *ኤሎሀ ጸባዖት*
4. አቤቱ ብርቱ ጌታ፣ መዝ. 89:8 – *ያህ* (መዝ. 68:4)፤ "ብርቱ" የሚለው ቅጽል (ቢዲቢ 340) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ።

**89፡6-8** እነዚህ ጥያቄዎች ዘወትር በሁለት መልኩ ነው ጥቅም ላይ የሚውሉት።

1. የአሀዳዊነት ማረጋገጫ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት
2. የአምልኮተ ባዕድ ጣዖታትን ማንኳሰሻ መንገድ (መዝ. 82፡1 ሊሆን ይችላል)

**89፡8 "እውነትህም ይከብብሃል"** ይህ ሐረግ ለመረዳት አዳጋች ነው። አንዳንድ ታሳቢዎች፡

1. እውነት ያህዌን እንደ ልብስ ከብቦታል
2. እሱ በነገር ሁሉ የታመነ ነው (አእት)
3. እሱ ጽኑ ነው (አኢመቅ፣ ማለትም፣ ለቃሉ)

**89፡10 "ረዓብ"** ይህ (ቢዲቢ 923) ሊያመለክት የሚችለው

1. የውኃ ነውጥ ዘንዶ (መዝ. 74፡12-17፣ ማለትም፣ የባቢሎናውያን የፍጥረት መግለጫ፣ ማስታወሻዬን ተመልከት በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር፣ የዘፍጥረት 1-11 መግቢያ
2. ግብፅ (ማለትም፣ በያህዌ ድል መነሣቷ እና ዘጸአት፣ ኢሳ. 51፡9-11)

## መዝሙር ፡ 89፡11-18

**11ሰማያት የአንተ ናቸው፥ ምድርም የአንተ ናት
ዓለምንና ሞላውም አንተ መሠረትህ።
12ሰሜንና ደቡብን አንተ ፈጠርህ
ታቦርና አርሞንዔም በስምህ ደስ ይላቸዋል።
13ክንድህ ከኃይልህ ጋር ነው
እጅህ በረታች ቀኝህም ከፍ ከፍ አለች።
14የዙፋንህ መሠረት ጽድቅና ፍርድ ነው
ምሕረትና እውነት በፊትህ ይሄዳሉ።
15እልልታ የሚያውቅ ሕዝብ ምስጉን ነው
አቤቱ፥ በፊትህ ብርሃን ይሄዳሉ።
16በስምህ ቀኑን ሁሉ ደስ ይላቸዋል፥
በጽድቅህም ከፍ ከፍ ይላሉ
17የኃይላቸው ትምክሕት አንተ ነህና፥
በሞገስህም ቀንዳችን ከፍ ከፍ ይላልና።
18ረድኤታችን ከእግዚአብሔር
ከንጉሣችንም ከእስራኤል ቅዱስ ነውና።**

**89፡11-18** ይህ አንጓ ያህዌን ያመሰግናል፣ እንዲሁም የእርሱ ሕዝቦች እንደምን የተባረኩ እንደሆኑ ይገልጻል።

1. ያህዌ
   ሀ. ሰማያት የእርሱ ናቸው
   ለ. ምድር የእርሱ ናት ፣ እርሱ ስለመሠረታቸው (ማለትም፣ ያህዌ ፈጣሪ ነው፣ መዝ. 24፡1-2፤ 78:69ለ፤ 102:25፤ ኢሳ. 51፡13፣16)
   ሐ. ሰሜንና ደቡብ የተፈጠሩት በእርሱ ነው (ምናባዊ ተመሳሳይነት ከኢዮብ 26፡7 ጋር)
   መ. የታቦርና የአርሞንኤም ተራሮች ሰውኛ ሆነዋል፣ ለስሙም እልል ይላሉ (መዝ. 65፡12፤ 98:8)
   ሠ. ኃይሉ (ማለትም፣ እጅ ወይም ክንድ፣ መዝ. 89፡10፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ) ማድረጉ ይመሰገናል
      (1) ጠንካራ ክንድ አለው
      (2) እጁ ብርቱ ነው
      (3) ቀኙ ከፍ ብላለች
   ረ. ከባሕርያቱ አራቱ ሰውኛ ሆነዋል፣ እንደ አካሉና ግዛቱ ባሕርይ (መዝ. 97፡2)

(1) ጽድቅ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ)
(2) ፍርድ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፈራጅ፣ ፍትሕ፣ ፍርድ)
(3) ቸርነት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቸርነት [ሄሰድ])
(4) እውነት/ታማኝነት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ ታማኝነት በብኪ)

ሰ. እሱ "የእስራኤል ቅዱሱ" ነው (መዝ. 71:22፤ 78:41: ኢሳ. 1:4፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቅዱሱ)

2. የእርሱ ሕዝብ

ሀ. የመለከቱን ድምጽ የሚሰሙት እነርሱ ብፁዓን ናቸው (ማለትም፣ የመቅደስ አምልኮ)
ለ. በፊቱ ብርሃን ተመላለሱ ("ፊት" እሱም የያህዌን አካላዊ መገኘት የሚያመለክት፣ መዝ. 90፡8)
ሐ. ቀኑን ሁሉ በስሙ ደስ ይበላችሁ (ማለትም፣ የአምልኮ መቼት ወይም ወታደራዊ ድል)
መ. በያህዌ ጽድቅ ከፍ ማለት (ማለትም፣ ቅዱስ ባሕርይ እና መገለጥ)
ሠ. ያህዌ የእነርሱ ክብር እና ኃይል ነው (መዝ. 28፡8)
ረ. ቀንድ (ማለትም፣ ኃይል፣ ተከባሪነት (ከፍ ያለ አቋም)
ሰ. ጥበቃ ("ጋሻ") ያህዌ ነው (መዝ. 47፡9)
ሸ. ንጉሡም ደግሞ የያህዌ ነው

"የእኛ" የሚለው ተውላጠ ስም መዝ. 89፡17-18 የሚያመለክተው፣ ያህዌ የእስራኤልን ንጉሥ እንደ ራሱ (የጥበቃ/ድል ቀንድ እና ጋሻ" እንደሚጠቀምበት ነው (ማለትም፣ ከረ-ሸ)።

**89፡12 "ሰሜንና ደቡብ"** እነዚህ ሁለት ቃላት የሌሎች ተጨማሪ ሁለት ተራሮች ስሞች ናቸው ማለት ይቻላል (ማለትም፣ ዛፎን፣ ማለትም፣ የበአል ተራራ ስም፣ ከዑጋሬት በስተሰሜን፤ እና ያሚን ወይም የታረመው ተያያዥ አማና፣ በደቡብ ቱርክ የሚገኝ ተራራ፣ ሰሎ. 4፡8)። ይህም ከታቦርና ከአርሞንኤም ጋር ትይዩ ይፈጥራል።

አብዛኞቹ ተርጓሚዎች እነርሱን የሚወስዱት እንደ ኮምፓስ ትይዩ ነጥቦች ነው፣ የያህዌን እንደ ፈጣሪ ሁለንተናዊ ንግሥና የሚያሳይ።

**89፡16 "ስምህ... ጽድቅህ"** እነዚህ ትይዩ ሲሆኑ ሁለቱም የሚጠቅሱት ያህዌን ራሱን ነው።

**89፡17 "ቀንድ"** ይህ የኃይል ፈሊጥ ነው (መዝ. 75:10፤ 89:24፤ 92:10፤ 148:14)፣ ከእንስሳት ግዛት ላይ የተወሰደ።

**89፡18 "ጋሻ... ንጉሥ"** እነዚህ ሁለቱም ያህዌን ሊጠቅሱ ይችላሉ ወይም እነርሱ ዳዊታዊ ንጉሥን ሊጠቅሱ ይችላሉ (መዝ. 89:19-29፤ መዝ. 84:10)፣ በእግዚአብሔር የተቀባው፣ ዓላማውን ለማስፈጸም።

**መዝሙር ፡ 89፡19-29**

**19 በዚያ ጊዜ ለልጆችህ በራእይ ተናገርህ**
**እንዲህም አልህ። ረድኤቴን በኃይል ላይ አኖርሁ**
**ከሕዝቤ የተመረጠውን ከፍ ከፍ አደረግሁ።**
**20 ባሪያዬን ዳዊትን አገኘሁት፥**
**ቅዱስ ዘይትም ቀባሁት።**
**21 እጄም ትረዳዋለች፥**
**ክንዴም ታጸናዋለች።**
**22 ጠላት በእርሱ ላይ አይጠቀምም፥**
**የዓመፃ ልጅም መከራ አይጨምርበትም።**
**23 ጠላቶቹን ከፊቱ እጠፋለሁ፥**
**የሚጠሉትንም አዋርዳቸዋለሁ።**
**24 እውነቴና ምሕረቴም ከእርሱ ጋር ነው፥**
**በስሜም ቀንዱ ከፍ ከፍ ይላል።**
**25 እጁን በባሕር ላይ**
**ቀኙንም በወንዞች ላይ አኖራለሁ።**
**26 እርሱ። አባቴ አንተ ነህ፥**
**አምላኬ የመድኃኒቴም መጠጊያ ይላል።**
**27 እኔም ደግሞ በኩሬ አደርገዋለሁ፥**
**ከምድር ነገሥታትም ከፍ ይላል።**
**28 ለዘላለምም ምሕረቴን ለእርሱ እጠብቃለሁ፥**
**ኪዳኔም በእርሱ ዘንድ የታመነ ነው።**
**29 ዘሩንም ለዓለምና ለዘላለም፥**
**ዙፋኑንም እንደ ሰማይ ዘመን አደርጋለሁ።**

**89፡19-29** ይህ አንጓ በተለይ ስለ ንጉሥ ዳዊት እና ስለ ይሁዳዊ ንጉሣዊ ዝርዮቹ ነው (2 ሳሙኤል 7)። እርሱ የመሲሕ ዓይነት/ተምሳሊት ሆኗል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሲሕ)።

ያህዌ ለሕዝቡ ተናግሯል (ጻድቅህ/የታመነው [ቢዲቢ 339]) ስለ እርሱ የተለየ መመረጥ፣ የእስራኤል ንጉሥ እንዲሆን (መዝ. 89፡19)።

1. ከፍ ብሏል፣ መዝ. 89፡19
2. ከሕዝቡ መሐል ተመርጧል፣ መዝ. 89፡19

3. ተገኝቷል፣ መዝ. 89፡20
4. ተቀብቷል፣ መዝ. 89፡20 (1 ሳሙ. 16፡1-13፤ ይህ የዕብራይስጥ ግሥ ነው፣ "መሲሕ" የሚለው መጠሪያ የመጣበት፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የብኪ መጠሪያዎች፣ ተለይቶ ለሚመጣው)
5. ጸንቷል፣ መዝ. 89፡21
6. በርትቷል፣ መዝ. 89፡21
7. አይስትም (ቢ.ዲ.ቢ. 674 II) ወይም መከራን አይቀበልም፣ 89፡22
8. ጠላቶቹ ይደቀቃሉ፣ መዝ. 89፡23
9. የያህዌ ሰውኛ ዘይቤዎች (ማለትም፣ ታማኝነት እና ቸርነት) ይጎዳኙዋል፣ መዝ. 89፡24
10. በያህዌ ስም ቀንዱ ከፍ ከፍ ይላል፣ መዝ. 89፡24
11. ግዛቱን ይቆጣጠራል፣ መዝ. 89፡25 (ማለትም፣ ከሜዲትራኒያን እስከ ኤፍራጥስ ወንዝ ድረስ፣ ዘጸ. 23፡31፤ ዘዳ. 1፡7-8)
12. እሱም እግዚአብሔርን በቅርብ ወዳጅነት መልኩ ይጠራል፣ መዝ. 89፡26
    ሀ. አባቴ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር አባታዊነት እና ልዩ ርዕስ፡ አባት)
    ለ. አምላኬ (ኤል)
    ሐ. የደኅንነቴ ዓለት (መዝ. 95፡1)
13. እሱም ይሾማል (ያለ ጾታዊ አገባብ) የክብር መጠርያ "በኵሬ" (2 ሳሙ. 7:14፤ 1 ዜና. 17:13፤ 22:10፤ 28:6፤ መዝ. 2:7)፣ መዝ. 89:27
14. ከምድር ነገሥታት ሁሉ ይልቃል (መዝ. 72:11፣ ግልጽ መሲሐዊ መጠሪያ፣ 1 ጢሞ. 6:15፤ ራዕ. 1:5፤ 17:14፤ 19:16፣ የያህዌ መጠሪያ ከዳን. 2:47፤ መንግሥቱ ሁለንተናዊ ነው ሚክያስ 5:4)፣ መዝ. 89:27
15. እንደ ቁ. 9፣ ሌላው ሰውኛ የያህዌ ባሕርይ፣ ለዘላለም ይጠብቀዋል፣ መዝ. 89:28
16. የያህዌ ኪዳን ያጸናዋል መዝ. 89:28 (መዝ. 89:3፣34)
17. ዝርዮቹም ይጸናሉ፣ ለዘላለምም ይገዛሉ፣ መዝ. 89:29 (መዝ. 89:4፤ 2 ሳሙኤል 7)

**89፡19 "በዚያን ጊዜ በራዕይ ተናገርከ"** ይህ ናታን ለዳዊት መናገሩን ነው የሚጠቅሰው፣ 2 ሳሙ. 7፡14-17።

▣ **"ረድኤቴን አድርጌአለሁ"** ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 1001፣ ኬቢ. 1438፣ ፒል የተጠናቀቀ) ፍችው ማበጀት ወይም ማኖር ማለት ነው።

"እኩሌታ" የሚለው ቃል ( ገזץ ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 740 I) በአንዳንድ ተርጓሚዎች መረዳትን ያገኘው እንደ

1. "ዘውድ" – ስኬት
2. "አክሊል" – አየተመቅ፣ አአመቅ

"አክሊል" የሚለው ቃል በኤምቲ ላይ ማሻሻያ ተደርጎበታል፣ የመጀመሪያውን ፊደል በመቀየር፣ ማለትም፣ ገזן ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 634፣ ዘጸ. 29:6፤ 39:30፤ ሌዋ. 8:9፤ 21:12፤ 2 ሳሙ. 1:10፤ 2 ነገ. 11:12፤ መዝ. 89:39፤ 32:18፤ ምሳ. 27:24፤ ዘካ. 9:16። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ለ "ዕርዳታ" ሀ ደረጃ ይሰጠዋል (እጅግ የላቀ ይሁንታ፣ ገጽ 354)።

**መዝሙር ፡ 89፡30-37**

**30ልጆቹ ግን ሕጌን ቢተዉ፥**
**በፍርዴም ባይሄዱ**
**31ሥርዓቴንም ቢያረክሱ፥**
**ትእዛዜንም ባይጠብቁ**
**32ኃጢአታቸውን በበትር፥**
**በደላቸውንም በመቅሠፍት እጐበኛታለሁ።**
**33ምሕረቴን ግን ከእርሱ አላርቅም፥**
**በእውነቴም አልበድልም**
**34ኪዳኔንም አላረክስም፥**
**ከከንፈሬም የወጣውን አልለውጥም።**
**35ዳዊትን እንዳልዋሸው**
**አንድ ጊዜ በቅዱስነቴ ማልሁ።**
**36ዘሩ ለዘላለም፥**
**ዙፋኑም በፊቴ እንደ ፀሐይ ይኖራል።**
**37ለዘላለም እንደ ጨረቃ ይጸናል**
**ምስክርነቱ በሰማይ የታመነ ነው። ሴላህ**

**89፡30-37** ይህ አንጓ አስደንጋጭ ተቃርኖ ነው፣ ያህዌ ለሕዝቡ ካለው አስደናቂ ዕቅድና ዓላማ አኳያ ("ከሆነ" የሚለውን፣ መዝ. 89፡30 እና 31 ላይ ተመልከት)።

1. ሕጌን ቢተዉ፣ መዝ. 89፡30
2. በፍርዱ ባይሄዱ፣ መዝ. 89፡30
3. ሥርዓቱን ቢያረክሱ፣ መዝ. 89፡31
4. ትእዛዙን ባይጠብቁ፣ መዝ. 89፡31

ያህዌ ገና ተከታታይ መግለጫዎችን ይሰጣል፣ ምን እንደሚያደርግና ምን እንደማያደርግ፣ ምንም እንኳ እስራኤል ባለማመን ውድቀት ላይ ቢገኝም። እሱ ታማኝ ነው!

1. ስለ ኃጢአታቸው እቀጣቸዋለሁ፣ መዝ. 89፡32
2. ምሕረቴን ግን ከእነርሱ አላርቅም፣ መዝ. 89፡33

3. በእውነቴም አልበድልም፣ 89፡33
4. ኪዳኔንም አላረክስም፣ መዝ. 89፡34
5. ከከንፈሬም የወጣውን አልለውጥም፣ መዝ. 89፡34
6. ዳዊትን እንዳልዋሽሁ አንድ ጊዜ በቅዱስነቴ ማልሁ፣ መዝ. 89፡35
   ሀ. ዘሩ ("ዘር") ለዘላለም ይኖራል፣ መዝ. 89፡36
   ለ. ዙፋኑም እንደ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ሰማይ ጸንቶ ይኖራል፣ መዝ. 89፡36ለ-37 (ለጸና የፍጥረት ሥርዓት ኤር. 31፡35-37)

ይህም የሁኔታዊ እና ሁኔታዊ ያልሆነውን ተስፋ ተቃርኖ (ክርክር) የሚያሳይ ነው። ይሄንን ጉዳይ በሁለት ስፍራዎች ላይ ገልጫለሁ።

1. ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን
2. ለዋንኛው የራዕይ መግቢያ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የብኪ የወደፊቱ ትንቢቶት አልያም (በተቃርኖ) የአኪ ትንቢቶች፣ በተለይም "ሦስተኛው ተቃርኖ"

ይኸው ተመሳሳይ ተቃርኖ፣ ሁኔታዊ በሆነና ሁኔታዊ ባልሆነ ተስፋ መካከል፣ በተቃርኖ ተመልክቷል፣ በኢሳይያስ አጽንዖታዊ መግለጫዎች፣ ማለትም ኢየሩሳሌም ፈጽሞ አትወድቅም በሚለው (ኢሳይያስ 37) እና በኤርምያስ አጽንዖት ማለትም እሷ ትወድቃለች፣ በይሁዳ አመንዝራነትና ለኪዳን አለመታዘዝ ሳቢያ በሚለው መካከል።

የተሻለው ግምት የሚሆነው፣ በታሪካዊ ውድቀቱ ላይ ይሄንን መዝሙር ለመጥቀስ፣ የዳዊታዊ ንጉሥ ግዞት ነው፣ አንድም በፈርዖን ኒካሁ II ወይም በናቡከደነፆር II። ይህ ግምት ብቻ ነው፤ መዝሙሩ ራሱ ታሪካዊ መቼቱን በግልጽ አያመለክትም። የሆነ ዓይነት መለኮታዊ ፍርድ ዳዊታዊው ንጉሥ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል።

**89፡30-31 "ሕግ... ፍርድ... ሥርዓት... ትዕዛዛት"** እነዚህ ሁሉ ትይዩ ቃላት ናቸው፣ ለያህዌ መገለጥ፣ በቅዱስ ቃሉ ላይ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ለእግዚአብሔር ራዕይ ቃላት።

**መዝሙር ፡ 89፡38-45**

**38አንተ ግን ናቅኸው ጣልኸውም፥**
**የቀባኸውንም ጣልኸው።**
**39የባሪያህንም ኪዳን አፈረስህ፥**
**መቅደሱንም በምድር አረከስህ።**
**40ቅጥሩን ሁሉ ጣልህ፥**
**አምባዎቹንም አጠፋህ።**
**41መንገድ አላፊም ሁሉ ተናጠቀው፥**
**ለጎረቤቶቹም ስድብ ሆነ።**
**42የጠላቶቹንም ቀኝ ከፍ ከፍ አደረግህ፥**
**ጠላቶቹንም ሁሉ ደስ አሰኘህ።**
**43የሰይፉንም ረድኤት መለስህ፥**
**በሰልፍም ውስጥ አልደገፍኸውም።**
**44ከንጽሕናውም ሻርኸው፥**
**ዙፋኑንም በምድር ጣልህ።**
**45የዙፋኑንም ዘመን አሳነስህ፥**
**በእፍረትም ሸፈንኸው። ሴላህ።**

**89፡38-45** ያህዌ በኪዳናቱ ላይ ካለው ታማኝነት በሰጠው መግለጫ አኳያ (በተለይ፣ አብርሃምና ዳዊት) እሱም ሕዝቡን ስለ ኃጢአታቸው ይፈርድባቸዋል (መዝ. 89፡32)። ፍርዱም የከፋና እስራኤል ሊረዳው የማይችል ዓይነት ነው (ተከታታይ የተጠናቀቁዎች)።

1. የቀባውን ጣለው
2. የቀባውንም ናቀው (ያልፎ አልፎ ቃል፣ ቢዲቢ 611፣ ኬቢ 658፣ ሰቆ. 2፡7)
3. የቀባውንም ፈጽሞ ተቆጣ
4. የባርያውንም ኪዳን አፈረሰ
5. አክሊሉንም አዋረደ
6. ቅጥሮቹንም አፈረሰ (የኢየሩሳሌምን)
7. ዐምባዎቹንም አጠፋ
8. መንገድ አላፊ እንዲናጠቀው አደረገ
9. ለጎረቤቶቹም ስድብ እንዲሆን አደረገ
10. የጠላቶቹን ኃይል ከፍ አደረገ
11. ጠላቶቹ እንዲደሰቱ አደረገ
12. እንዲሸነፍ አደረገ
13. ክብሩም እንዲቀር አደረገ (ከታች ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)
14. ዙፋኑንም በምድር ጣለ
15. ዘመኑን አሳነሰ
16. በእፍረት ከደነው

ዋው! እንዴት ያለ ፍርድ ነው! እግዚአብሔር ይመስገን፣ ስለ መዝ. 89፡33-37። እግዚአብሔር ስለ አኪ ይመስገን፣ ስለ ወንጌል፣ ስለ ኢየሱስ ሕይወት፣ ትምህርት፣ ሞት፣ እና ትንሣኤ!

**89:44**
**አአመመቅ፣ ጀፒኤስአኤ**

| | |
|---|---|
| **የተእመቅ** | **“ግርማ”** |
| **አኪጀት፣ ፔሺታ** | **“ክብር”** |
| **አየተመቅ፣ አእቅ** | |
| **አኢመቅ** | **“በትረ-መንግሥቱን ከእጁ ላይ”** |
| **LXX** | **“ንጽሕና”** |

ቃሉ ( ነገהט מ ፣ ቢዲቢ 372፣ UBS “ሀ” ደረጃ አለው) እዚህጋ ብቻ ነው የሚከሰተው፣ ብኪ ላይ። የተባዕታይ (ወንዴ) ጾታው ስም መሠረታዊ ፍቺ “ንጽሕና” ወይም “የላቀ መሆን” ማለት ነው፣ እሱም ከግሡ የመጣ። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 356) የሚለው አአመመቅ ወይም LXX እንደሚከተሉት ነው። ማረሚያው( מהט ) የ አየተመቅ ከትይዩው ጋር በተሻለ ይገጥማል፣ መዝ. 89:44ለ ላይ ካለው።

**89፡41-48** ይህ አንጓ ጥያቄ ይጠይቃል፣ በመዝሙር ላይ ተደጋግሞ የሚነሣውን፡ “እስከ መቼ?” (መዝ. 6:3፤ 13:1፤ 74:10፤ 79:5፤ 80:4፤ 90:13፤ 94:3)።

የዚህ አንጓ የተለየ ገጽታ ጥያቄዎቹ አይደሉም፣ ነገር ግን ያህዌ እንዲሠራ የተሰጡት ምክንያቶች እንጂ (መዝ. 89፡47፡51)።

1. አስብ (ቃል ተተኳሪ) የሰውን ሕልውና ደካማነት፣ መዝ. 89፡47-48
2. አስብ (ቃል ተተኳሪ) ቸርነትህን እና ታማኝነትህን ለዳዊት የገባኸውን ቃል
3. አስብ በአሕዛብ መካከል በሕዝብህ ላይ የደረሰውን መሣለቅ
4. አስብ የቀባኸው መሣለቂያ እንደሆነ

ከፍ የሚል የመዋጀት ዕቅድ አለ፣ እስራኤልንና መሲኁን የሚያካትት። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

**መዝሙር ፡ 89፡46-48**

**[46]አቤቱ፥ እስከ መቼ**
**ለዘላለም ፊትህን ትመልሳለህ?**
**እስከ መቼስ ቍጣህ እንደ እሳት ይነድዳል?**
**[47]ችሎታዬ ምን እንደ ሆነ አስብ**
**በውኑ የሰውን ልጅ ሁሉ ለከንቱ ፈጠርኸውን?**
**[48]ሕያው ሆኖ የሚኖር፥ ሞትንስ የማያይ ማን ነው?**
**ነፍሱንስ ከሲኦል እጅ የሚያድን ማን ነው? ሴላህ።**

**89፡46 “እሳት”** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እሳት።

**መዝሙር ፡ 89፡49-51**

**[49]ለዳዊት በእውነት የማልህ፥ አቤቱ፥**
**የቀድሞ ምሕረትህ ወዴት ነው?**
**[50]አቤቱ፥ የባሪያዎችህን ስድብ፥**
**በብብቴ ብዙ አሕዛብን የተቀበልሁትን፥**
**[51]አቤቱ፥ ጠላቶችህን የሰደቡትን**
**የቀባኸውን ዘመን የሰደቡትን አስብ።**

**89፡49 “ጌታ ሆይ”** ይህ ቃል አዶን ነው (ማለትም፣ ጌታ፣ ባለቤት፣ ጌታ)። እሱም በድጋሚ መዝ. 89፡50 እንደሚከሰት ተመልከት፣ ነገር ግን መዝ. 89፡51 ላይ ያህዌ ነው። የእግዚአብሔር የኪዳን ስም ይህን መዝሙር ሸፍኖታል (5 ጊዜ)።

**መዝሙር ፡ 89፡52**

**[52]እግዚአብሔር ለዘላለም ይባረክ።**
**ይሁን ይሁን።**

**89፡52** እግዚአብሔር ያከናውነዋል! እሱ ሁሉቱንም ነው፣ ትክክለኛና መሐሪ። እሱም ለቃሉ እውነት ነው!

ይህ ሐረግ የመዝሙር 89 ክፍል አይደለም፣ ነገር ግን የመዝጊያ ቡራኬ ነው፣ የመጽሐፍ III፣ የመዝሙር (ማለትም፣ ሌሎቹ መጻሕፍትም በቡራኬ ነው የሚዘጉት፣ መዝ. 4:14፤ 72:18-19፤ 106:48)።

▣ **“አሜን”** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሜን።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወስን አይደለም።

1. ይህን መዝሙር በሙሉ አንብበው፤ የመዝሙሩ ርዕሰ-ጉዳይ ምንድነው?
2. ሁኔታዊ ባልሆነ ኪዳንና ሁኔታዊ በሆነ ኪዳን መካከል ያለውን ልዩነት አብራራ።
3. "ቸርነት" እና "ታማኝነት"ን ግለጽ።
4. ይህ መዝሙር ከ2 ሳሙኤል 7 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
5. ብኪ የሜሶፖታሚያን፣ የግብፅን፣ እና የከነአንን አፈ-ታሪክ ይጠቀማልን? እንደዛ ከሆነ፣ ለምን?
6. የእስራኤል ንጉሥ የእግዚአብሔር ልጅ እንዴት ይሆናል?
7. ይህ መዝሙር መሲሐዊ ገጽታ አለውን? እንደዛ ከሆነ፣ እንዴት?

# መዝሙር 90
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የአምላክ ዘላለማዊነትና የሰው ጊዜያዊነት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የሙሴ የእግዚአብሔር ሰው ጸሎት | የአምላክ ዘላማዊነትና የሰው ደካማነት | ጸሎት ከብሔራዊ ጠላት ለመታደግ | ስለ እግዚአብሔርና ስለ ሰው ልጆች | ስለ ሰዎች ደካማነት |
| 90:1-2 | 90:1-2 | 90:1-2 | 90:1-2 | 90:1 |
| | | | | 90:2 |
| 90:3-6 | 90:3-6 | 90:3-6 | 90:3-6 | 90:3-4 |
| | | | | 90:5-6 |
| 90:7-12 | 90:7-12 | 90:7-10 | 90:7-8 | 90:7-8 |
| | | | 90:9-10 | 90:9-10 |
| | | 90:11-12 | 90:11-12 | 90:11 |
| | | | | 90:12-13 |
| 90:13-17 | 90:13-17 | 90:13-17 | 90:13-17 | 90:14-15 |
| | | | | 90:16-17 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

5. የመጀመሪያው አንቀጽ

6. ሁለተኛው አንቀጽ

7. ሦስተኛው አንቀጽ

8. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የያህዌን ዘላለማዊነት ያውጃል (ማለትም፣ መዝ. 90:1-2፣ 4) እና የሰው ልጅን ጊዜያዊነት (ማለትም፣ መዝ. 90:3፣ 5-6፣ 9-10)፡፡

ለ. የእስራኤል ኃጢአት (ማለትም፣ መዝ. 90:8) ያህዌ በራሱ ሕዝብ ላይ ፍርድን እንዲያመጣ አደረገው (ማለትም፣ መዝ. 90:7፣9፣11)፡፡ እነርሱም ምሕረቱ እንዲመለስ ለመኑ (ማለትም፣ መዝ. 90:12፣ 13-17)።

ሐ. ይህ መዝሙር በርካታ ቃላት አሉት በድርብ ጥቅም ላይ የዋሉ፡፡

1. ተመለስ፣ ዞር – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ እና ከዚያም *ቃል* ተተኳሪ፣ መዝ. 90:3
2. ተደሰት… አስደስተን – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል* ተጓዳኝ እና ከዚያም *ፒል* ተተኳሪ

3. ታየ... ተከሰተ – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ ቃል የተጠናቀቀ፣ ከዚያም ኒፋል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
4. አረጋግጥ... አስረግጥ– ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 464፣ ሁለቱም ፖሰል ተተኳሪ

መ. በአስገራሚ መልኩ የኤምቲ የመግቢያ ማስታወሻ ሙሴ ደራሲው እንደሆነ ይገልጻል፡፡ እነዚህ ማስታወሻዎች በሙት ባሕር ጥቅል ላይ አይገኙም፣ ነገር ግን በሴፕቱዋጂንት ላይ ይገኛሉ፡፡ እነርሱ ጥንታዊ የአይሁድ ወጎች ናቸው፣ ነገር ግን በዋነኛነት የተመስጧዊው ጽሑፍ ክፍል አይደሉም፡፡ ይህ መዝሙር በሙሴ የተገለጸበት ታሳቢ ምክንያቶች
1. ከዘፍ. 3፡19 ጋር ግልጽ የሆነው ጠቃሽ /ማለትም፣ ለአቧራ የተለያዩ ቃላት ነገር ግን አንድ ዓይነት ጽንሰ-ሐሳብ/
2. ታሳቢ ጠቃሽ፣ በመካከል
   ሀ. መዝ. 90፡2፣ እና ዘዳ. 32፡6፣18
   ለ. መዝ. 90፡2፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት እና ዘዳ. 32፡40
   ሐ. መዝ. 90፡13ለ፣ ኀዘኔታ እና ዘዳ. 32፡36
3. በመጽሐፍ IV መዝሙር ላይ፣ የሙሴ ስም በርካታ ጊዜ ተከስቷል (መዝ. 99:6፤ 103:7፤ 105:26፤ 106:16፣23፣32) እናም አንድ ጊዜ ብቻ በመጀመሪያዎቹ ሦስቱ መጻሕፍት ላይ (ማለትም፣ መዝ. 77:20)፡፡
   በሞላው በአራተኛው በመዝሙር ምድብ /መዝሙር 90-106/ ሦስት መዝሙሮች ብቻ ልማዳዊው ደራሲ ተሰጥቷል፡፡
   ሀ. መዝሙር 90፣ ሙሴ
   ለ-ሐ. መዝሙር 103 እና 104 ለዳዊት ተሰጥተዋል
   LXX ሁሉንም መዝሙራት ለዳዊት ይሰጣል፣ ከመዝሙር 90 በቀር፡፡

ሠ. ይህ መዝሙር በርካታ ቃላት አሉት /እና ሐረጋት/ ጊዜን የሚገልጹ፡፡
1. በሁሉም ትውልዶች፣ መዝ. 90፡1
2. ከዘላለም እስከ ዘላለም፣ መዝ. 90፡2
3. ሺህ ዓመት፣ መዝ. 90፡4
4. ትላንት፣ መዝ. 90፡4
5. የሌሊት ትጋት፣ መዝ. 90፡4
6. በማለዳ፣ መዝ. 90:5፣6፣14
7. ወደ ምሽት ሲል፣ መዝ. 90:6
8. ቀናችንን ሁሉ፣ መዝ. 90:9፣14
9. ዘመናችን እንደ እስትንፋስ፣ መዝ. 90:9
10. የሕይወታችን ቀናት፣ መዝ. 90:10
11. ሰባ ዓመት፣ መዝ. 90:10
12. ሰማንያ ዓመት፣ መዝ. 90:10
13. የቀኖቻችን ቁጥር፣ መዝ. 90:12
14. ምን ያህል ይሆናል፣ መዝ. 90:13
15. እንደ ቀናቶቹ አኳኋን፣ መዝ. 90፡15
16. ክፉ ባየንባቸው ቀናት፣ መዝ. 90፡15

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 90፡1-2**

**[1]አቤቱ፥ አንተ ለትውልድ ሁሉ መጠጊያ ሆንህልን።**
**[2]ተራሮች ሳይወለዱ፥**
**ምድርም ዓለምም ሳይሠሩ፥**
**ከዘላለም እስከ ዘላለም ድረስ አንተ ነህ።**

**90፡1-2** ይህ አንጓ ሦስት ሥነ-መለኮታዊ እውነቶችን ያስተዋውቃል፡፡
1. እስራኤል የያህዌ የተለየ ሕዝብ ነበር፣ ነውም /ማለትም፣ ከአብርሃም መጠራት ጀምሮ፣ ዘፍ. 12፡1-3 ላይ/፡፡
2. ያህዌ ዘላለማዊ አምላክ ነው፣ መጀመሪያና መጨረሻ የሌለው (መዝ. 9:7፤ 29:10፤ ኢሳ. 41:4፤ 43:10፤ 44:6፤ 48:12፤ ይሁዳ ቁ. 25፤ ራዕ. 1:8፣17፤ 21:6፤ 22:13፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አህዳዊነት/፡፡
3. ያህዌ የሥጋዊው ዓለም ፈጣሪ ነው፣ ለገዛ ራሱ ዓላማ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

**90፡1 "ጌታ"** አአመመቅ 1970 ዕትም "ጌታ" የሚል አለው (ማለትም፣ ያህዌ) ነገር ግን ኤምቲ *ኤዶን* የሚል ነው ያለው (መዝ. 90:17)። አአመመቅ 1995 ዕትም ይሄንን አርሞታል። አኪጀት፣ አእቅ፣ እና የተእመቅ ደግሞ ጌታ (ያህዌ) የሚል አላቸው፣ ይኸውም መዝ. 90:13 ላይ የሚገኝ።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**
**አየተመቅ** **"መኖርያ ስፍራ"**

**አእቅ** **"ቤት"**
**አኢመቅ፣ ጀፒኤስአኤ፣**
**የተእመቅ፣ LXX** **"መጠጊያ"**

ኤምቲ "መኖርያ ስፍራዎች" ( מָעוֹן ፣ ቢዲቢ 732 I፣ መዝ. 71:3)። አአመመቅ የግርጌ ማስታወሻ "መጠጊያ ስፍራ" በሚል ይጠቅሳል ( מָעוֹז ፣ ቢዲቢ 731፣ መዝ. 27:1፤ 37:40) እንደ ጥንታዊ አማራጭ። ሁለቱም ጽንሰ-ሐሳቦች አንድ ላይ ተጠቅሰዋል፣ መዝ. 91:9 ላይ፣ በትይዩ።

**90:2** የመጀመሪያዎቹ ሁለቱ የቅኔ ስንኞች አካላዊ ፍጥረትን ሰውኛ ያደርጉታል፣ በሰው ልደት ዘይቤ ቃላት።

1. መወለድ፣ ኢዮብ 15:7፤ ምሳ. 8:25
2. መውለድ፣ በጥሬው "በምጥ ሕመም ላይ መጠማዘዝ፣" ቢዲቢ 297፣ ፖለል ቁ. 2፤ እሱም ያህዌ እስራኤልን ሲወልድ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ዘዳ. 32:6፣18 ላይ

▣ **"ምድር... ዓለም"** እነዚህ ትይዩ ናቸው የታሰበ ልዩነት የሌላቸው (መዝ. 19:4፤ 24:1፤ 33:8፤ 77:18)። ሁለተኛው ቃል ለዩኒቨርስ የቆመ አይመስለኝም። መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ፕላኔት (ዓለም) ነው። ለመጀመሪያው ቃል፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር።

▣ **"ከዘላለም እስከ ዘላለም"** ይህ ከበርካቶቹ ፈሊጣዊ ሐረጎች አንደኛው ነው፣ የያህዌን ዘላለማዊነት የሚገልጹት። ያህዌ የሚለው ስሙ፣ ፍችው "ከዘላላም እስከዘላለም፣ ሕያው" ማለት ነው ዘጸ. 3:14)።

ለ"ከዘላለም እስከ ዘላለም" (ቢዲቢ 761) ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (ኦላም)።

እኔ ዘወትር እጠይቃለሁ እግዚአብሔር ከየት እንደ መጣ። መጽሐፍ ቅዱስ ይሄንን ጥያቄ አይመልስም፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ሕልውናና ድርጊት ይጀምራል፣ ዘፍ. 1:1 ላይ። የማወቅ ፍላጎታችን መጠበቅ ይኖርበታል! ከምርመራ ተጠበቁ፣ ራዕይ በሌለበት!

### መዝሙር ፡ 90፡3-6

**3 ሰውን ወደ ኅሳር አትመልስም**
**የሰው ልጆች ሆይ፥ ተመለሱ ትላለህ**
**4 ሺህ ዓመት በፊትህ**
**እንዳለፈች እንደ ትናንት ቀን፥**
**እንደ ሌሊትም ትጋት ነውና።**
**5 ዘመኖች የተናቁ ይሆናሉ፥**
**በማለዳም እንደ ሣር ያልፋል።**
**6 ማልዶ ያብባል ያልፋልም፥**
**በሠርክም ጠውልጎና ደርቆ ይወድቃል።**

**90፡3-6** የመጀመሪያው አንጓ ለያህዌ ዘላለማዊነት አጽንዖት እንደሚሰጥ፣ ይህ አንጓ የሚያስረግጠው የሰውን ልጅ ጊዜያዊነት እና ደካማነት ነው። ይህም በሦስተኛው አንጓ ላይ ተብራርቷል (መዝ. 90፡7-12) ያህዌ በእስራኤል ላይ በወሰደው እውነታ። የእግዚአብሔር የተለዩ ሕዝቦች እንኳ የኃጢአትን ዋጋ ያጭዳሉ!

**90፡3** ይህ ቁጥር እውነታዊ መግለጫን ይሰጣል (ማለትም፣ ሰዎች ይሞታሉ፣ ዘፍ. 2:7፤ 3:14፣16) እና ከተመሳሳይ ቃል ጋር ትይዩ ነው (ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427) በተተኳሪ ዓረፍተ ነገር። የሰው ሞት የእግዚአብሔር ፍቃድ አልነበረም፣ ወይም የእርሱ ፕላኔት ተፈጥሯዊ ሂደት፣ ነገር ግን የሰው ኃጢአት ቀጥተኛ ውጤት እንጂ! የሚላርድ ኢሪክሰንን *ክርስቲያን ሥነ-መለኮት* ተመልከት 2ኛ ዕትም፣ ገጽ 1176-1177።

ይህ የአሁኑ ዓለም ያህዌ በመጀመሪያ ያሰበው አይደለም፣ ነገር ግን የዘፍጥረት 3 ውጤት እንጂ።

▣ **"የሰው ልጆች ሆይ"** በግልጽ ከዘፍጥረት ከመጠቀሱ የተነሣ፣ ይህ ሊሆን የሚችለው "የአዳም ልጆች" ነው (አኢመቅ፣ መዝ. 8፡4)።

**90፡4** ይህ ፈሊጣዊ ቋንቋ ነው፣ ለያህዌ ዘላለማዊነት (2 ጴጥ. 3፡8)። ይህ የሚያሳየው የጊዜ አመላካቾች እንደ ዘይቤአዊ ፈሊጥ ጥቅም ላይ መዋላቸውን ነው (ማለትም፣ "ቀን" የዘፍጥረት 1፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቀን (ዮም)። ጊዜ ለመለኮት ወሳኝ ነገር አይደለም፣ ለሰው ልጅ እንደሆነው!

ለ "ሺህ" ከታች ያለውን ልዩ ርዕስ ተመልከት።

ልዩ ርዕስ፡ ሺህ (እልፍ)

▣ **"የሌሊት ትጋት"** ብኪ ላይ ሌሊቱ በሦስት ትጋቶች ይከፋፈላል (ማለትም፣ ወታደራዊ መንገድ፣ የሰዓቱ ርዝመት የሚከፋፈልበት፣ ወታደሮች ዘብ የሚቆሙበት)። በአኪ የፍልስጥኤም አይሁድ የሮሜን ክፍልፋይ ወስደዋል፣ ባለ አራት የሌሊት ትጋቶች።

1. ብኪ – ዘጸ. 14:24፤ መሳ. 7:19፤ 1ሳሙ. 11:11፤ ሰቆ. 2:19
2. አኪ – ማቴ. 14:35፤ ማርቆስ 13:35

**90፡5** **"እንደ ጎርፍ"** የጎርፍ ውኃ ዘወትር በዘይቤነት ጥቅም ላይ የሚውለው ለሰዎች ችግር ነው። ሆኖም፣ እዚህ ቃሉ ሊሆን የሚችለው ነጠላ የቃል አጠቃቀም ነው፣ ፍችውም፣ "ሕይወትን ወደ ፍጻሜ ማምጣት" የሚል (ኬቢ 281 I፤ ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 1150)፣ የዓረብ ሥርን ተከትሎ፣ እናም ከዕብራይስጥ ሥር ጋር አይዛመድም፣ "መፍሰስ" (ቢዲቢ 281፣ ኬቢ 281 II)።

▣ **"መተኛት"** መተኛት (ቢ.ዲ.ቢ. 446) የብኪ. ፈሊጥ ነው፣ ለሞት። የመጀመሪያው ክስተት የሚዛመደው መሪዎች ወደ ወገናቸው ሲከማቹ ነው (ማለትም፣ ዘዳ. 31፡16)። እሱም ለሚሞቱት ሁሉ ፈሊጥ እየሆነ መጣ (ማለትም፣ መዝ. 13፡3፤ ዳን. 12፡2፤ ኢሳ. 26፡19)። ይህ ፈሊጥ በሞትና በትንሣኤ መካከል ያለውን ንቁ ያልሆነ አቋም አያመለክትም።

▣ **"እንደ ሣር"** ይህ ተደጋጋሚ ዘይቤ ነው፣ ለሰው ልጅ (ኢዮብ 14፡2፤ መዝ. 102፡11፤ 103፡15፤ ኢሳ. 40፡6፤ 1 ጴጥ. 1፡24፣25)። ወቅታዊ ዕፅዋት በመጸው ታይተው በክረምት እንደሚጠፉ፣ እንዲሁ የሰው ልጅ አጭር የሕይወት ዕድሜ ይኖረዋል!

በአንዳንድ ጽሑፎች እሱ የሚያመለክተው የኃጢአተኞችን ጥፋት ነው (ኢዮብ 18፡16፤ መዝ. 37፡2)። ወቅታዊ ሣር ይጠፋል (ማለትም፣ ለታማኝ ተከታዮች ተስፋ አለ)፣ ነገር ግን ኃጢአተኞች ለዘላለም ይሞታሉ።

ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ ይህ መዝሙር በልጅነት (ሳይበስሉ) መሞትን ሊያመለክት ይችላል (ማለትም፣ በተለይ መዝ. 90፡10መ)።

***መዝሙር ፡ 90፡7-12***

**7 እኛ በቍጣህ አልቀናልና፥**
**በመዓትህም ደንግጠናልና።**
**8 የተሰወረውን ኃጢአታችንን በፊትህ ብርሃን፥**
**በደላችንንም በፊትህ አስቀመጥህ።**
**9 ዘመናችን ሁሉ አልፎአልና፥**
**እኛም በመዓትህ አልቀናልና ዘመኖቻችንም እንደ ሸረሪት ድር ይሆናሉ።**
**10 የዘመኖቻችንም ዕድሜ ሰባ ዓመት፥**
**ቢበረታም ሰማንያ ዓመት ነው**
**ቢበዛ ግን ድካምና መከራ ነው**
**ከእኛ ቶሎ ያልፋልና፥ እኛም እንገሠጻለንና።**
**11 የቍጣህን ጽናት ማን ያውቃል?**
**ከቍጣህ ግርማ የተነሣ አለቁ።**
**12 በልብ ጥበብን እንድንማር፥**
**ቀኝህን እንዲህ አስታውቀን።**

**90፡7-12** ይህ አንጓ በግልጽ የሚቀበለው ያህዌ በሕዝቡ ላይ የወሰደው ፍርድ የኃጢአታቸው ቀጥተኛ ውጤት መሆኑን ነው። ሆኖም፣ ሕዝቡ በእግዚአብሔር መሠረታዊ ባሕርይ ይታመናሉ፣ ተስፋም ያደርጋሉ— በምሕረቱ! ለእኔ መዝ. 103፡8-14 ርግጠኛ ተስፋ ነው፣ በእግዚአብሔር ምሕረት (ዘጸ. 34፡6፤ ዘኍ. 14፡18፤ ዘዳ. 4፡31፤ ነህ. 9፡17፤ መዝ. 86፡15፤ 145፡8)።

**90፡7 "ቁጣ"** የተለያዩትን ቃላት ተመልከት፣ በኪዳን አለመታዘዝ ላይ ያህዌ የመሰደውን አቋም የሚገልጹትን።

1. ንዴት፣ መዝ. 90፡7ሀ፣11 – ቢ.ዲ.ቢ. 60 I
2. ቁጣ፣ መዝ. 90፡7ለ – ቢ.ዲ.ቢ. 404
3. ቁጣ፣ መዝ. 90፡9፣11 – ቢ.ዲ.ቢ. 720

መጽሐፍ ቅዱስ የሰዎችን ቃላት እንደሚጠቀም አስታውሱ፣ እግዚአብሔርን ለመግለጽ። እሱም ዘወትር ዘይቤአዊና ውስን ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሲገለጽ። መዝሙር 103 ረድቶኛል ቁጣውንና ፍቅሩን ለማመዛዘን! ኢየሱስ የእርሱ ባሕርይና ተስፋዎች የመዳረሻ መግለጫ ነው!

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኢመቅ** | ***"መደንገጥ"*** |
| **አኪጀት፣ አእቅ** | ***"መሸበር"*** |
| **አየተመቅ** | ***"መሸነፍ"*** |
| **ጀፒኤስአኤ** | ***"በሽብር መመታት"*** |

ይህ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 96፣ ኬቢ. 111፣ *ኒፋል የተጠናቀቀ*) የሞትን ፍርሃትና ፍርድን ነው (መዝ. 30፡7፤ 104፡29፤ ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 610-611)። ኃጢአት ጊዜያዊና ፍጻሜያዊ ውጤቶች አሉት!

**90፡8 "በፊትህ ብርሃን"** ብርሃን ለመልካምነት፣ ለራዕይ፣ ለጤና መጽሐፍ ቅዱሳዊ ተምሳሊት ነው። እግዚአብሔር ብርሃን ነው (1 ጢሞ. 6፡16፤ ያዕቆብ 1፡17፤ 1 ዮሐንስ 1፡5)። የእርሱ አካላዊ መገኘት በፊቱ ብርሃን ፈሊጥ ይገለጻል (መዝ. 4፡6፤ 31፡16፤ 44፡3፤ 67፡1፤ 80፡3፣7፣19፤ 89፡15፤ 104፡2፤ 119፡135)።

**90፡11 "ከግርማህ ፍርሃት የተነሣ"** "ፍርሃት" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 432) የተዛባ መረዳት ሊኖረው ይችላል። እሱ የሚገልጸው አክብሮትን፣ ክብርን፣ ርኅራኄን ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፍርሃት)። ደካማውና ጊዜያዊው ለዘላለማዊው እውቅና ይሰጣል። ለቅዱሱ! ምሳሌ ይህን ጽንሰ-ሐሳብ እንዴት እንደተጠቀመ ተገንዘብ (ምሳ. 10፡27፤ 14፡26-27፤ 15፡16፤ 19፡23፤ 22፡4፤ 23፡17)።

**90፡12** የእኛን ደካማነትና የእርሱን ቋሚነት አንዴ ከተገነዘብን፣ ከዛን በኋላ እና ከዛን በኋላ ብቻ የደስታ፣ የሰላም፣ እና የመታመን ሕይወትን መኖር እንችላለን። ተስፋችን ሙሉ ለሙሉ በእርሱ ላይ ነው። ለእርሱ የምንሰጠው አገልግሎት ለሕይወት ትርጉም ይሰጠዋል!

1. አስተምረን – ቢ.ዲ.ቢ. 393፣ ኬቢ. 390፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
2. እንሆን ዘንድ – ቢ.ዲ.ቢ. 97፣ ኬቢ. 112፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ* በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

▣ **"ልብ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ።

***መዝሙር ፡ 90፡13-17***

**[13]አቤቱ፥ ተመለስ፥ እስከ መቼስ ነው?**
**ስለ ባሪያዎችህም ተምዋገት።**
**[14]በማለዳ ምሕረትህን እንጠግባለን**
**በዘመናችን ሁሉ ደስ ይለናል ሐሤትም እናደርጋለን።**
**[15]መከራ ባሳየኸን ዘመን ፈንታ፥**
**ክፉም ባየንባቸው ዘመኖች ፋንታ ደስ ይለናል።**
**[16]ባሪያዎችህንና *ሥራህን* እይ፥**
**ልጆቻቸውንም ምራ።**
**[17]የአምላካችን የእግዚአብሔር ብርሃን በላያችን ይሁን፦**
**የእጆቻችንንም *ሥራ* በላያችን አቅና።**

**90፡13-17** ይህ የመጨረሻ አንጓ በንስሐ የጸሎት ጥያቄ የተሞላ ነው፣ በያህዌ ባሕርይ ላይ በመመሥረት።

1. ተመለስ መዝ. 90፡13 – ቢ.ዲ.ቢ. 996፣ ኬ.ቢ. 1427፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 90፡3 – ወደ አፈር እንመለሳለን፣ እሱ ወደ ምሕረቱ ይመለሳል!
2. በማዘን፣ መዝ. 90፡13 – ቢ.ዲ.ቢ. 636፣ ኬ.ቢ. 688፣ *ኒፋል ተተኳሪ*
3. አጥግበን፣ መዝ. 90፡14 – ቢ.ዲ.ቢ. 959፣ ኬ.ቢ. 1302፣ *ፒል ተተኳሪ*
   ሀ. በደስታ እንዘምር ዘንድ – ቢ.ዲ.ቢ. 943፣ ኬ.ቢ. 1247፣ *ፒል ተጓዳኝ*
   ለ. መደሰት – ቢ.ዲ.ቢ. 970፣ ኬ.ቢ. 1333፣ *ቃል ተጓዳኝ*
4. ደስ አሰኘን፣ መዝ. 90፡15 – ቢ.ዲ.ቢ. 90፣ ኬ.ቢ. 1333፣ *ፒል ተተኳሪ*
5. *ሥራህ* ለአገልጋዮችህ ይገለጥ፣ መዝ. 90፡16 – ቢ.ዲ.ቢ. 906፣ ኬ.ቢ. 1157፣ *ኒፋል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
6. ግርማህ ለልጆችህ፣መዝ. 90፡16 – እንደ ቁ. 5 ተመሳሳይ ግሥ ይመስላል
7. የጌታ የአምላካችን ሞገስ በእኛ ላይ ይሁን፣ መዝ. 90፡17 – ቢ.ዲ.ቢ. 224፣ ኬ.ቢ. 243፣ *ቃል ተጽዕኖዊ*
8. የእጃችንን *ሥራ* አጽና፣ መዝ. 90፡17 – ቢ.ዲ.ቢ. 465፣ ኬ.ቢ. 464፣ *ፖለል ተተኳሪ*
9. ቁ. 8 ተደግሞ ነው

በዚህ አንጓ ላይ ምን ያህል ግሦች በ ש እንደሚጀምሩ ተገንዘብ
1. ተመለስ፣ መዝ. 90፡13 – ቢ.ዲ.ቢ. 996
2. አጥግብ፣ መዝ. 90፡14 – ቢ.ዲ.ቢ. 959
3. በደስታ መዘመር፣ መዝ. 90፡14 – ቢ.ዲ.ቢ. 943
4. መደሰት፣ መዝ. 90፡14 – ቢ.ዲ.ቢ. 970
5. አስደስተን፣መዝ. 90፡15 – ቢ.ዲ.ቢ. 970
6. አይተናል፣ መዝ. 90፡15 – ቢ.ዲ.ቢ. 906
7. ተገልጧል፣ መዝ. 90፡16 – ቢ.ዲ.ቢ. 906

**90፡13 "እስከ መቼስ ነው?"** ይህ ተደጋጋሚ ጥያቄ ነው (መዝ. 6፡8፤ 13፡1፤ 74፡10)። በዚህ ሕይወት *ሥቃይና* ችግርን የሚቀበሉ አማኞች ወደ እግዚአብሔር ይጮኻሉ!

ራዕይ እንጂ ሁኔታዎች ሳይሆኑ አመለካከትህንና በእግዚአብሔር ላይ ያለህን እምነት እንደሚገልጹ ርግጠኛ ሁን። ሁኔታዎች ይመጣሉ፣ ይሄዳሉም እግዚአብሔር ግን ይኖራል!

**90፡14 "ምሕረት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት (ሄሰድ)።

**90፡15** ይህ ቁጥር የጸሎት ጥያቄ ነው፣ ወደ ፊት የሚኖሩት የበረከት ዓመታት፣ ካለፉት የመከራ ዓመታት ጋር እንዲገጥሙ።

የእስራኤል ችግሮች በኃጢአትዋ እግዚአብሔር የላካቸው መሆኑን መዝሙረኛው እንደተረዳ ተገንዘብ (ማለትም፣ መዝ. 31፡10፤ 39፡11)!

**90፡16-17** መዝ. 90፡16 የሚያተኩረው በያህዌ *ሥራዎች* ላይ መሆኑን ተገንዘብ እንዲሁም መዝ. 90፡17 በታማኝ ተከታዮች *ሥራዎች*። የያህዌ ማዳን ሕዝቡ ከትውልድ ወደ ትውልድ እንዲበለጽጉ ያደርጋል። ኃጢአት ሁሉንም ነገር ያጠፋል!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የጥንታዊ አይሁድ ወጎች የዚህ መዝሙር ጸሐፊ ሙሴያዊ መሆኑን የሚያስረግጡት ለምድነው?
2. መዝሙሩ ዘፍጥረት 3ን የሚጠቅስባቸውን መንገዶች ዘርዝር።
3. የዚህን መዝሙር ማዕከላዊ እውነት በአንድ ዓረፍተ ነገር ግለጽ።
4. መዝ. 90፥10 የሚናገረው ከረጅም ዕድሜ በኋላ ያለን ሞት ነው ወይስ ያለ ዕድሜ (በልጅነት) መሞትን?
5. የመዝ. 90፥13-17 የጸሎት ጥያቄዎች ዘርዝር።

# መዝሙር 91
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ደኅንነት በጌታ ለሚታመን<br><u>ኤምቲ መግቢያየለውም</u> | በእግዚአብሔር መገኘት የመኖር ደኅንነት | የታማኝ ጠባቂ የሆነውን አምላክ ደጅ መጥናት | እግዚአብሔር ጠባቂያችን | በእግዚአብሔር ጥበቃ ሥር |
| 91:1-4 | 91:1-2 | 91:1-6 | 91:1-6 | 91:1-2 |
| | 91:3-6 | | | 91:3-4 |
| | | | | 91:5-6 |
| 91:5-10 | 91:7-8 | 91:7-8 | 91:7-8 | 91:7-9 |
| | 91:9-10 | 91:9-10 | 91:9-13 | |
| | | | | 91:10-11 |
| 91:11-13 | 91:11-13 | 91:11-13 | | |
| | | | | 91:12-13 |
| 91:14-16 | 91:14-16 | 91:14-16 | 91:14-16 | 91:14-16 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

*ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።*

*ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡*

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*

2. *ሁለተኛው አንቀጽ*

3. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መግቢያ
1. ይህ አስደናቂ መዝሙር ነው፣ የእግዚአብሔርን ጥበቃና ከታማኝ ተከታዮቹ ጋር መገኘቱን የሚገልጽ (መዝሙር 16፤ 23፤ 62፤ 121)።
2. መዝሙራት ዘወትር ስለ እስራኤል ሕዝብ ነው የሚናገሩት (መዝሙር 90)፣ ይሄኛው ግን ግለሰባዊ ሆኗል (ነጠላ ቁጥር “አንተ”)።
3. የመዝ. 91:1-8 እውነቶች ከመዝ. 91:9-13 ጋር ትይዩ ሆነዋል። የእግዚአብሔር ክብካቤና መጋቢነት ለአጽንዖት ተደግመዋል፣ ከዚያም በኋላ እግዚአብሔር ራሱ መዝ. 91:14-16 ላይ ይናገራል።

ለ. መዝሙር 91 ላይ ጥቅም ላይ የዋሉት የመለኮት ስሞች (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች)።
1. ልዑሉ (ኤሊኦኝ ቢዲቢ 751፣ ኬቢ 832)፣ መዝ. 91:1ሀ – ገላጭ መጠሪያ፣ በቅኔ ላይ ተዘውትሮ ጥቅም ላይ የሚውል
2. ሁሉን ቻይ (ሻዳ፣ ቢዲቢ 994)፣ መዝ. 91:1ለ፣ 9ለ፣ ብዙ ጊዜ ዘፍጥረትና ኢዮብ ላይ ጥቅም ላይ የሚውል፤ 68:14 እና እዚህ – አባታዊ ስም ለእግዚአብሔር (ዘጸ. 6:30፤ ከዕብራይስጥ ሥር ሊሆን ይችላል “ብርቱ መሆን” ከሚለው ኒዶቴ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 401)
3. ጌታ (ያህዌ፣ ቢዲቢ 217)፣ መዝ. 91:2ሀ፣ 9ሀ – የመለኮት የኪዳን ስም፣ በቅድሚያ ዘፍ. 2:4 ላይ ጥቅም ላይ የዋለ፤ እሱም ከዕብራይስጥ “የመሆን” ግሥ ነው (ዘጸ. 3:14)፤ ራቢዎች የሚሉት፣ እሱ መለኮትን እንደ አዳኝ፣ ተቤዢ ነው የሚገልጸው
4. እግዚአብሔር (ኢሊሖኝ ቢዲቢ 43)፣ መዝ. 91:2ለ – ይህ የመለኮት አጠቃላይ (የወል) ስም ነው በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ኤል፤ ዘፍ. 1:1 ላይ የብዙ ቁጥሩ ኤሎሂም ጥቅም ላይ ውሏል፤ ራቢዎች የሚሉት ይህ የሚገልጸው እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ፣ መጋቢ፣ እና ሰጪ ነው፣ በምድር ላለ ፍጥረት ሁሉ

ሐ. ይህ መዝሙር ባልተጠናቀቁዎች ተሞልቷል (28)፣ ይኸውም የአምላካችንን ድርጊቶች ቀጣይነት የሚገልጽ፣ በታማኝ ተከታዮች አኳያ።

የመዝ. 91:14 ሁለቱ የተጠናቀቁዎች የሚገልጹት የደረጀውን፣ የቅርብ ግንኙነት ነው፣ በእግዚአብሔርና በእርሱ ታማኝ ተከታዮች መካከል። ከጋብቻ ሕይወት ምናባዊ ምስያ (ኢሳ. 54:5፤ ሆሴ. 2:19፤ ኤፌ. 5:25)።

1. "የተያያዘ" – ዘፍ. 2:24
2. "ማወቅ" – ዘፍ. 4:1፣17፣25፤ 24:16፤ 38:26

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 91፡1-4**

**[1]በልዑል መጠጊያ የሚኖር**
**ሁሉን በሚችል አምላክ ጥላ ውስጥ ያድራል።**
**[2]እግዚአብሔርን፡- አንተ መታመኛዬ ነህ እለዋለሁ**
**አምላኬና መሸሸጊያዬ ነው፥ በእርሱም እታመናለሁ።**
**[3]እርሱ ከአዳኝ ወጥመድ**
**ከሚያስደነግጥም ነገር ያድንሃልና።**
**[4]በላባዎቹ ይጋርድሃል፥**
**በክንፎቹም በታች ትተማመናለህ**
**እውነት እንደ ጋሻ ይከብብሃል።**

**91፡1-4** ይህ አንጓ በርካታ ስሞችን/መጠሪያዎችን ለመለኮት ይጠቀማል (ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ለ) እንዲሁም በርካታ ዘይቤዎችን፣ የእርሱን ክብካቤና ደጋፊነት ለመግለጽ።

1. መጠጊያ – መዝ. 27:5፤ 31:20፣ እሱም መቅደሱን የሚገልጽ፣ መዝ. 27:5፤ 31:20፤ 32:7፤ 61:4
2. ጥላ – ልዩ ርዕስ ተመልከት: ጥላ እንደ ዘይቤ፣ ለመጠጊያና ለክብካቤ
3. መጠጊያ – ማስታወሻ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ተመልከት መዝ. 5:11 ላይ
4. ምሽግ – መዝ. 18:2፤ 31:3፤ 71:3፤ 144:2፤ ኤር. 16:19

መዝሙር 91:4 ቁ. 2፣ 3፣4ን ይጠቅሳል፣ ከላይ

ታማኝ ተከታዮች የሚታመኑበት አንዱ (ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ ቃል ያልተጠናቀቀ፤ ማስታወሻ ተመልከት ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር መዝ. 4:5 ላይ)።

1. ከአዳኞች ወጥመድ አዳናቸው (መዝ. 124:7)
2. ከክፉ ነገር አዳናቸው (መዝ. 91:6፤ አጋንንታዊ ሊሆን ይችላል፣ ዕን. 3:5 እና ልዩ ርዕስ፡ አጋንንታዊ በብኪ)
3. በክንፎቹ ይጋርዳቸዋል (መዝ. 36:7፤ 57:1፤ 63:7)
4. ታማኝነቱ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ)
   ሀ. ጋሻ (መዝ. 35፡2)
   ለ. ምሽግ ወይም (የተመት) ጋሻ (ሁለቱም ወታደራዊ ቃላት፣ ይህ ቃል [ቢዲቢ 695፣ ኬቢ 750] የሚገኘው እዚህጋ ብቻ ነው፣ ብኪ ላይ፤ ኒዶቲ፣ ቅጽ 3 ገጽ 243)

ይህ የተዋበና ኃይለኛ አንጓ ነው፣ ስለ መለኮት ባሕርይና ድርጊቶች፣ በሕዝቡ አኳያ።

**91፡1 "በልዑል ጥላ"** ይህ ሊያመለክት የሚችለው

1. የኪሩቤልን ክንፎች ነው፣ በታቦቱ ላይ (ማለትም፣ የኪዳን ከለላ፣ ዘጸ. 25፡17-22)
2. የጠባቂ እናት ወፍ ክንፎች (መዝ. 17:8፤ 36:7 57:1፤ 61:4፤ 53:7፤ 91:4፤ እና ማቴ. 23:27)
3. ከፀሐይ ሙቀት ቃጠሎ መከለያ (መዝ. 121:5፤ ኢሳ. 25:4፤ 32:2)

**91:2 "በምታመንበት"** ይህ ቁልፍ ነው ከእግዚአብሔር ጋር ላለ ኪዳናዊ ግንኙነት (መዝ. 4:5፤ 25:2፤ 56:4)።

**91፡3 "ቸነፈር"** መሠረታዊው ሥር ገበገ ነው (ቢዲቢ 182-184)፣ እሱም በርካታ አጠቃቀሞች ያሉት።

1. ቃል (LXX የመዝ. 91:3)
2. መናገር (ኤር. 5:13)
3. ቸነፈር (ዘጸ. 5:3፤ 9:15፤ ዘኍ. 14:12፤ ሌዋ. 26:25፤ ዘዳ. 28:21፤መዝ. 78:50)
4. መስክ (መሰማሪያ)(ሚኪያስ 2:12)
5. ንብ ወይም የንብ መንደፊያ (ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 916)

በመዝ. 91:5-6 ምክንያት ቁ. 3 ከይዘቱና ከትይዩው ጋር በተሻለ የሚገጥም ይመስላል።

**መዝሙር ፡ 91፡5-10**

**[5]ከሌሊት ግርማ፥**
**በቀን ከሚበርር ፍላጻ፥**
**[6]በጨለማ ከሚሄድ ክፉ ነገር፥**

**ከአደጋና ከቀትር ጋኔን አትፈራም።**
**[7]በአጠገብህ ሺህ**
**በቀኝህም አሥር ሺህ ይወድቃሉ**
**ወደ አንተ ግን አይቀርብም።**
**[8]በዓይኖችህ ብቻ ትመለከታለህ፥**
**የኃጥአንንም ብድራት ታያለህ።**
**[9]አቤቱ፥ አንተ ተስፋዬ ነህና**
**ልዑልን መጠጊያህ አደረግህ።**
**[10]ክፉ ነገር ወደ አንተ አይቀርብም፥**
**መቅሠፍትም ወደ ቤትህ አይገባም።**

**91፡5-10** ይህ አንጓ ይቀጥላል፣ የመዝ. 91፡1-4ን ምናባዊ ምስያ፣ በተለይም "ከሚያስደነግጥም ክፉ ነገር" የመዝ. 91፡3ለ፣ እሱም መዝ. 91፡5-6 ላይ የተስፋፋ፣ ወታደራዊው ምናባዊ ምስያ መዝ. 91፡4ሐ ላይ ያለው ደግሞ መዝ. 91፡7-8 ላይ ተስፋፍቷል።

**91፡5-6** እነዚህ ነገሮች በራቢዎች የሚታዩት እንደ ኢጋንንታዊ ነገሮች ነው (ኢንሳይክሎፔዲያ ጁዲሲያ፣ ቅጽ 5 ገጽ 1523)። ተገንዘብ (1) እሱ እንደሚራመድ፣ መዝ. 91፡6 እና (2) "እሱ" የመዝ. 91፡7። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኢጋንንታዊ በብኪ።

**91፡7** ይህ ግነታዊ ዘይቤ ገለጻ ነው፣ ወታደራዊ ምስያን የሚያሳይ፣ ለአማኝ ግለሰብ የሚደረገውን ክብካቤ፣ በኪዳን አምላኩ።

**91፡8** የእግዚአብሔር ሰዎች የክፉዎች ጥቃት እንደሚደርስባቸው ሁሉ፣ የእነርሱን ፍርድ የሚታዘቡ ይሆናሉ (መዝ. 37:34፤ 54:7፤ 58:10)።

▣ **"ብድራት"** ይህ ዓይነቱ የመሠረታዊ ሥር ዓይነት (ቢዲቢ 1024) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ። ተመሳሳይ መልኮች ዘዳ. 32፡35፤ ኢሳ. 59፡18 (ሁለቴ) ላይ ይገኛሉ።

**91፡9-10** ይህ ትይዩ ነው ከመዝ. 91፡1-2 ጋር፤ መዝ. 91፡10 ከመዝ. 91፡5-7 ጋር ትይዩ እንደሆነ ሁሉ።

**91፡9** ይህ ቁጥር በዕብራይስጥ በቅድሚያ የሚመለከት የሚመስለው ወደ እግዚአብሔር ነው (ማለትም፣ አቤቱ ያህዌ) በስንኙ ላይ፣ ከዚያም በኋላ ወደ ታማኝ ተከታይ የሚያመለክት ዓረፍተ ነገር ይሠራል፣ እሱን ማደሪያ ስፍራ ያደረገውን። በርካታ ስፍራዎች አሉ፣ በዚህ ዓይነት አካላትን (ባለቤትን) በመደባለቅ የሚከሰቱበት። የዩቢኤስ *ማስታወሻ መጽሐፍ* (ገጽ 801) ሐሳብ የሚያቀርበው

1. መዝ. 91፡1፣ ካህኑ ነው የሚናገረው
2. መዝ. 91፡2፣ አምላኪው (ምዕመኑ)
3. መዝ. 91፡3-8፣ ካህን በድጋሚ
4. መዝ. 91፡9ሀ፣ አምላኪው (ምዕመኑ)
5. መዝ. 91፡9ለ፣ ካህኑ በድጋሚ
6. መዝ. 91፡14-16፣ እግዚአብሔር ይናገራል

ይህ አንዳንድ የግለሰብ (ባለቤት) ችግሮችን ያቃልላል፣ ነገር ግን ሌሎች ሰዋሰዋዊ ጉዳዮችን ያስነሣል። የዕብራይስጥ ቋንቋ ዘወትር ግለሰቦችን ይቀይራል፣ ጸታ እንኳ ሳይቀር፣ ግልጽ ባልሆነ ምክንያት።

### መዝሙር ፡ 91፡11-13

**[11]በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ**
**መላእክቱን ስለ አንተ ያዝዛቸዋልና**
**[12]እግርህም በድንጋይ እንዳትሰናከል**
**በእጆቻቸው ያነሡሃል።**
**[13]በተኵላና በእባብ ላይ ትጫማለህ**
**አንበሳውንና ዘንዶውን ትረግጣለህ።**

**91፡11-12** እነዚህ ቁጥሮች በሰይጣን ተጠቅሰዋል፣ ኢየሱስ በምድረ-በዳ በተፈተነበት ጊዜ (ማቴ. 4፡6፤ ሉቃስ 4፡10-11)። የእግዚአብሔር ክብካቤ ተስፋ የጽሑፍን አቃቂር በማውጣት መሆን የለበትም፣ ቀደም ብሎ በተገመተ ጥያቄ። አማኞች መከራን ይቀበላሉ (ኢዮብ፤ መዝሙር 72 አልያም ዘዳግም 27-28፤ እና ሮሜ 8:28-30 አልያም 8:31-39)።

**91፡11 "መላእክቱ"** ይህ የብኪ ዳራ ሊሆን ይችላል (ዘጸ. 23:20 ተመልከት) ከማቴ. 18:10፤ ሉቃስ 4:10-11 (LXX) እና ሐዋ. 12:15 ጋር፣ "ከጠባቂ መላእክት" ጽንሰ-ሐሳብ ጋር። ደግሞም ተመልከት፣ ዕብ. 1፡14ን ከመዝ. 103፡21 ጋር ብትደባልቅ፣ ግንኙነት ያላቸው ይመስላሉ።

▣ **"በመንገድህ ሁሉ ይጠብቁህ ዘንድ"** ይህ አስደናቂ ተስፋ ነው በእግዚአብሔር ለሚታመኑና ወደ ጥበቃው (ክብካቤው) ለሚሸሹ። ሆኖም፣ ይህም ደግሞ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ግነታዊ ዘይቤ ነው። የምንኖረው በወደቀ፣ ክፉ ዓለም ነው። አማኞች መከራ፣ ሕማም፣ ፈተና ወዘተ... ይገጥማቸዋል፣ (ማቴ. 5:10-12፤ ዮሐንስ 15:18-21፤ 16:1-3፤ 17:14፤ ሐዋ 14:22፤ ሮሜ. 5:3-4፤ 8:17፤ 2 ቆሮ. 4:16-18፤ 6:3-10፤ 11:23-30፤ ፊሊ. 1:29፤ 1 ተሰ. 3:3፤ 2 ጢሞ. 3:12፤ ያዕቆብ 1:2-4፤ 1 ጴጥ. 3:14፤ 4:12-16፤ ራዕ. 11:7፤ 13:7)።

**91፡13** ይህ የቀደሙትን ተስፋዎች ከታሪካዊነት አኳያ፣ ከምድረ-በዳ መንከራተት ዘመን ጋር ያያይዘዋል፣ ወይም እሱ ዘይቤአዊ ቋንቋ ሊሆን ይችላል፣ ሰዎች ስለሚገጥማቸው ችግሮች፣ በወደቀው ዓለም (መዝ. 58፡3-5፤ ሉቃስ 10፡19)።

**መዝሙር ፡ 91፡14-16**

**[14]በእኔ ተማምኖአልና አስጥለዋለሁ**
**ስሜንም አውቆአልና እጋርደዋለሁ።**
**[15]ይጠራኛል እመልስለትማለሁ፥**
**በመከራውም ጊዜ ከእርሱ ጋራ እሆናለሁ**
**አድነዋለሁ አከብረውማለሁ።**
**[16]ረጅምን ዕድሜ አጠግበዋለሁ፥**
**[0]ማዳኔንም አሳየዋለሁ።**

**91፡14-16** እግዚአብሔር ይናገራል እናም "እንዲህ ከሆነ… ከዚያም" የሚል የኪዳናዊ ባርኮት ግንኙነት አዘጋጅቷል (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)።

| | እግዚአብሔር (ከዚያም) | አማኝ (እንዲህ ከሆነ) | የእግዚአብሔር በረከቶች |
|---|---|---|---|
| 1. | ያድነዋል | ይወዳል ("ይጣበቃል" እግዚአብሔርን (የተጠናቀቀ) | ከእርሱ ጋር ይሆናል፣ በችግር ጊዜ |
| 2. | ያከብረዋል | የአምላከን ስም ያውቃል (የተጠናቀቀ) | ይታደገዋል |
| 3. | ይመልስለታል | እግዚአብሔርን ሲጠራ (የተጠናቀቀ) | ያከብረዋል (ዮሐንስ 12፡26) |
| | | | ሀ. በረጅም ዕድሜ |
| | | | ለ. የእግዚአብሔርን ማዳን ያያል |

**91፡14 "ማወቅ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የብኪ ምስያ የሆኑትን መጠጊያ፣ ጥላ፣ መሸሸጊያ/ምሽግ አብራራ።
2. የእግዚአብሔርን ስሞች ዘርዝር፣ ግለጽም።
3. መዝ. 91፡5-7 የሚናገረው ስለ ኢጋንንታዊ ነው፣ ስለ ውጊያ፣ ወይስ ስለ ሕማም?
4. መዝ. 91፡9-10 የመዝ. 91፡1-2ን ሐሳብ ለምን ደገመ?
5. ሰይጣን ይሄንን መዝሙር እንዴት አላግባብ ተጠቀመበት፣ ስለ ኢየሱስ በመናገር?
6. ይህ መዝሙር የሚሰጠው ተስፋ እውነተኛ አማኞች ችግር እንደማይገጥማቸው ነውን?
7. "ስም" የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ አብራራ፣ ከመዝ. 91፡14-15 ጋር በተያያዘ።

# መዝሙር 92
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ምስጋና ለጌታ መልካምነት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የሰንበት ቀን መዝሙር | ምስጋና ለጌታ ስለ ፍቅሩ እና ታማኝነቱ | ምስጋና ከግለሰባዊ ጠላቶች መታደግ በኋላ | የምስጋና መዝሙር | የጻድቅ መዝሙር |
| 92:1-4 | 92:1-4 | 92:1-4 | 92:1-4 | 92:1-3 |
| | | | | 92:4-6 |
| 92:5-9 | 92:5-7 | 92:5-9 | 92:5-8 | |
| | | | | 92:7-8 |
| | 92:8-9 | | 92:9-11 | 92:9-11 |
| 92:10-15 | 92:10-11 | 92:10-11 | | |
| | 92:12-15 | 92:12-15 | 92:12-15 | 92:12-13 |
| | | | | 92:14-15 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የግብርና እድገት ቃላትን ይጠቀማል፣ እንደ መዝ. 1፡3፣ የአንዱን መንፈሳዊ ሕይወት ለመግለጽ።
1. በአሉታ
   ሀ. ኃጢአተኞች እንደ ሣር ሲበቅሉ፣ መዝ. 92፡7
   ለ. ዓመጻ የሚያደርጉ ሁሉ ሲለመልሙ፣ መዝ. 92፡7
2. በአዎንታዊ
   ሀ. ጻድቅ ሰው ይለመልማል፣ መዝ. 92፡12
   ለ. እሱም ያድጋል፣ መዝ. 92፡12
   ሐ. በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተተክሏል፣ መዝ. 92፡13
   መ. በአምላካችንም አደባባይ ውስጥ ይበቅላሉ፣ መዝ. 92፡13
   ሠ. ያን ጊዜ በለመለመ ሽምግልና ያፈራሉ፣ መዝ. 92፡14
   ረ. እነርሱም ፍሬአማ እና እጅግ ለምለም ይሆናሉ፣ መዝ. 92፡14

ለ. ተደጋጋሚ የቃላት አጠቃቀም አለ፣ በ.፺ የሚጀምር
1. መብቀል ("ቡቃያ")፣ መዝ. 92፡7 — ቢዲቢ 827፣ ኬቢ 965
2. ይለመልማሉ፣ መዝ. 92፡7 — ቢዲቢ 821፣ ኬቢ 950
3. መበተን ("መከፋፈል")፣መዝ. 92:9 – ቢዲቢ 825፣ ኬቢ 962
4. ዓመጻን የሚሠሩ ሁሉ፣ መዝ. 92:9 – ቢዲቢ 821፣ ኬቢ 950
5. መለምለም ( "ቡቃያ")፣ መዝ. 92:12 – ቢዲቢ እንደ ቁ. 1

6. መለምለም (“ቡቃያ”) – እንደ ቁ. 1

ሐ. የጸሎት ጥያቄ የለም (ማለትም፣ ተተኳሪዎች፣ ተጽዕኗዊዎች፣ ተጓዳኞች)፣ ትክክለኛ መግለጫዎች ለእግዚአብሔር ሥራዎች።
1. የእርሱ ባሕርይ፣ መዝ. 92፡2፣15
2. የእርሱ ሥራዎች
   ሀ. ፍጥረት፣ መዝ. 92፡5
   ለ. ፍትሕ፣ መዝ. 92፡6-9
   ሐ. ባርኮቶች፣ መዝ. 92፡10-14

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 92፡1-4**

**[1]እግዚአብሔርን ማመስገን መልካም ነው፥**
**ልዑል ሆይ፥ ለስምህም ዝማሬ ማቅረብ**
**[2]በማለዳ ምሕረትን፥**
**በሌሊትም እውነትህን ማውራት**
**[3]አሥር አውታር ባለው በበገና፥**
**ከምስጋና ጋርም በመሰንቆ።**
**[4]አቤቱ፥ በሥራህ ደስ አሰኝተኸኛልና**
**በእጅህም ሥራ ደስ ይለኛልና።**

**92፡1-4** ይህ አንጓ ለምስጋና አጽንዖት ይሰጣል። የዜማን ተደጋጋሚ ጥቅሻን ተመልከት።
1. ግሦች
   ሀ. አመስግኑ፣ መዝ. 92:1 – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ሂፊል ያልተወሰነ አወቃቀር
   ለ. ምስጋናን ዘምሩ፣ መዝ. 92:1 – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ፒዔል ያልተወሰነ አወቃቀር
   ሐ. ደስ ይበላችሁ፣ መዝ. 92:4 – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ ፒዔል የተጠናቀቀ
   መ. በደስታ ዘምሩ፣ መዝ. 92:4 – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ ፒዔል ያልተጠናቀቀ
2. የዜማ መሣርያዎች (ሀ. ተገልጸው ይሆናል ለ. እና ስለዚህ፣ ሁለት መሣርያዎች ብቻ ተገልጸዋል መዝ. 33:2፤ 144:9)
   ሀ. ባለ አስር አውታር በገና፣ መዝ. 92:3 – ቢዲቢ 797
   ለ. ማሲንቆ፣ መዝ. 92:3 – ቢዲቢ 614 II
   ሐ. በገና፣ መዝ. 92:3 – ቢዲቢ 490 (ለ. እና ሐ. ሁለቱም መዝ. 57፡8 ላይ ተጠቅሰዋል)

**92፡1 “ልዑሉ”** ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝሙር 91፡1 ላይ።

**92፡2** ይህ መዝሙር በሦስት ያልተወሰኑ ተናባቢዎች ይጀምራል።
1. ምስጋና ማቅረብ
2. ምስጋና መዘመር
3. ማወጅ – ቢዲቢ 616፣ ኬቢ 665፣ ሂፊል

የቁጥር 3፣ “ማወጅ፣” ደግሞ መዝሙሩን እንደሚዘጋ ተገንዘብ (*inclusio*) መዝ. 92:15 ላይ። አዋጁ የሚያካትታቸውም
1. የያህዌን ቸርነት፣ መዝ. 92:2 (ልዩ ርዕስ ተመልከት: ቸርነት [ሄሴድ])
2. የያህዌ ታማኝነት፣ መዝ. 92:2 (መዝ. 33:4፤ 143:1፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ እና ታማኝነት በብሉ)
3. የያህዌ ጻድቅነት፣ መዝ. 92:15 (ልዩ ርዕስ ተመልከት: ጽድቅ)
4. የያህዌ ጽናተና ብርታት (“እሱ ዓለቴ ነው”)፣መዝ. 92:15
5. የያህዌ ፍጹም ባሕርይ (“በእርሱ ዓመጻ የለበትምና” ሮሜ. 9:11፤ ያዕቆብ 1:17)፣ መዝ. 92:15

▣ **“በማለዳ... በሌሊት”** እነዚህ ትይዩዎችና ፈሊጣዊ ናቸው፣ ለ “ዘወትር።” ሌለኛው አማራጭ የሚሆነው፣ የዘወትሩን መሥዋዕት ጊዜያት ማንጸባረቃቸው ነው (ማለትም፣ 3 ሰዓት፣ 9 ሰዓት በመቅደስ፣ እና ስለዚህ የአምልኮ ሥርዓታዊ አጽንዖት አላቸው።)

**92፡4 “በሥራህ”** ሁለቱ ቅኔአዊ ስንኞች፣ የመዝ. 92፡4 ይህን ሐሳብ ደግመዋል (ማለትም፣ መዝሙር 1፣ ማለትም፣ “ሁለቱ መንገዶች፣” ዘዳ. 30፡15፣19)። የያህዌ ሥራ
1. የኃጢአተኛ ጥፋት፣ መዝ. 92:5-9 (በተለይ. መዝ. 92:5ሀ
2. የጻድቅ መባረክ፣ መዝ. 92:10-15

**መዝሙር ፡ 92፡5-9**

**[5]አቤቱ፥ ሥራህ እጅግ ትልቅ ነው፥**
**አሳብህም እጅግ ጥልቅ ነው።**
**[6]ሰነፍ ሰው አያውቅም።**

**ልብ የሌለውም ይህን አያስተውለውም።**
**[7]ኃጢአተኞች እንደ ሣር ሲበቅሉ**
**ዓመፃ የሚያደርጉ ሁሉ ሲለመልሙ፥**
**ለዘላለም ዓለም እንዲጠፉ ነው።**
**[8]አቤቱ፥ አንተ ግን ለዘላለም ልዑል ነህ**
**[9]አቤቱ፥ እነሆ፥ ጠላቶችህ ይጠፋሉና፥**
**ዓመፃንም የሚሠሩ ሁሉ ይበተናሉና።**

**92፡5-9** ይህ አንጓ የሚያተኩረው በያህዌ ድርጊት ላይ ነው፣

1. ሰነፍ ሰው መዝ. 92:6ሀ – ቢዲቢ 35 አወቃቀር ቢዲቢ 129
2. ልብ የሌለው ሰው፣ መዝ. 92:6ለ – ቢዲቢ 493፣ ሁለቱም ቁ. 1 እና ቁ. 2 መዝ. 49:10፤ 94:8 ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል
3. ኃጢአተኛ፣ መዝ. 92:7ሀ – ቢዲቢ 957
4. ዓመጻን የሚሠራ፣ መዝ. 92:7ለ
5. የያህዌ ጠላቶች፣ መዝ. 92:9 (ሁለቴ) – ቢዲቢ 33፣ *ቃል* ቦዝ አንቀጽ

የእነርሱም ባሕርይ

1. ምንም እውቀት የላቸውም
2. በዚህ በወደቀ ዓለም ላይ ለምልመዋል
3. በመዳረሻው እና በቋሚነት ይጠፋሉ (በዚህ ምክንያት ነው ሰነፍና ማስተዋል የሌለው የማያስተውሉት)

የያህዌ ባሕርይ

1. ታላላቅ ሥራዎች አሉት
2. ጥልቅ የሆነ ሐሳብ (*ቃል* ቢዲቢ 770 እዚህጋ ብቻ)
3. በልዑልነቱ ለዘላለም
4. መዝ. 92፡15 ለያህዌ የታማኝነት ሥራ የተደረገ ምስጋና ነው፣ ለታማኝ ተከታዮቹ

## መዝሙር ፡ 92፡10-15

**[10]ቀንዴ አንድ ቀንድ እንዳለው ከፍ ከፍ ይላል**
**ሽምግልናዬም በዘይት ይለመልማል።**
**[11]ዓይኔም በጠላቶቼ ላይ አየች፥**
**ጆሮዬም በእኔ ላይ በቆሙ በክፉዎች ላይ ሰማች።**
**[12]ጻድቅ እንደ ዘንባባ ያፈራል፥**
**እንደ ሊባኖስ ዝግባም ያድጋል።**
**[13]በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ ተተክለዋል፥**
**በአምላካችንም አደባባይ ውስጥ ይበቅላሉ።**
**[14]ያን ጊዜ በለመለመ ሽምግልና ያፈራሉ**
**ደስተኞችም ሆነው ይኖራሉ።**
**[15]አምላኬ እግዚአብሔር እውነተኛ እንደ ሆነ ይነግራሉ፥**
**በእርሱም ዘንድ ዓመፃ የለም።**

**92፡10-15** ይህ አንጓ የሚያተኩረው በያህዌ ድርጊቶች ላይ ነው፣ ለጻድቅ ሰው (መዝ. 92፡12)። የእርሱን ድርጊቶች ተመልከቱ፣ ለእነርሱ።

1. ቀንዱን ከፍ ያደርጋል
2. በአዲስ (ትኩስ) ዘይት ይቀባዋል
3. እንደ ዘንባባ ያፈራል
4. እንደ ዝግባ ያድጋል
5. በያህዌ መቅደስ ተተክሏል (መዝ. 52፡8)
6. በያህዌ አደባባይ ውስጥ ይበቅላል (መዝ. 65:4፤ 84:10፤ 135:2)
7. በሽምግልናውም ያፈራል
8. ርጥበታማና ለምለም ይሆናል
9. ያህዌ ዓለቱ እንደሆነ ያውቃል፣ እሱም ፍጹም ትክክል እንደሆነ

ራቢዎች ይሄንን አንጓ የሚተረጉሙት የፍጻሜ ዘመንን መቼት እንደሚጠቅስ ነው። ይህ እውነት ሊሆን ይችላል (መዝ. 92፡7ሐ)።

**92፡10 "የዱር በሬ"** LXX የዕብራይስጡን ቃል የሚተረጉመው ቢዲቢ 910፣ ᄀᄆᄌ ፣ እንደ "አንድ ቀንድ እንዳለው እንስሳ" ነው እሱም የኪንግ ጀምስን ትርጉም የሚከተል። አኪጀት ወደ "የዱር በሬ" ይቀይረዋል።

ይህ ቃል ርግጠኝነት የለውም (ኬቢ 1163)።

1. የዱር በሬ (ጎሽ) (የአካዲያን ሥር)
2. የዱር ጎሽ
3. ነጭ አጋዘን (የዓረብኛ ሥር)
4. ሳላ (ታርጉምስ)
5. አውራሪስ (ቫልጌት)

▣
**አአመመቅ፣ አኪጀት** **"ተቀብቻለሁ"**
**አየተመቅ** **"በእኔ ላይ አፈሰስክ"**
**አእቅ** **"ባርከኸኛልና"**
**አኢመቅ** **"ቀብተኸኛል"**
**ጀፒኤስኦኤ** **"ረስርሻለሁ"**
**LXX** **"ሽምግልናዬ"**
**ፔሺታ** **"እቀባለሁ"**

*ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 117፣ ኬ.ቢ. 134፣ *ቃል የተጠናቀቀ*) ዘወትር ፍችው "መደባለቅ" ነው፣ ወይም "ማደናገር"፤ እዚህጋ ብቻ ነው መቀባትን የሚገልጽ። ይህ ፍቺ ሊመጣ የሚችለው ከዓረብ ሥር ነው፣ "ማረስረስ" ከሚለው። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 363) "ረስርሻለሁ" ለሚለው የ "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ)።

**92፡11** ይህ መዝሙር የእስራኤልን ንጉሥ ምስጋና የሚያንጸባርቅ ከሆነ (LXX የሚለው ዳዊትንና "መቀባቱን" ነው፣ መዝ. 91፡10ለ)፣ እንግዲያውስ ይህ ቁጥር ሊያመለክት የሚችለው ሥርወ-መንግሥቱን ለመገልበጥ የተደረገ ሴራ ነው፣ የተገኘውን።

**92፡13 "ተተክሏል"** ይህ *ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 1060፣ ኬ.ቢ. 1570፣ *ቃል ተገብሮ አንቀጽ*) ፍችው "መተከል" ነው፣ እናም ተገብሮው የሚያመለክተው፣ በእግዚአብሔር (መዝ. 1፡3፤ ኤር. 17፡8፤ ሕዝ. 17፡10፣22፤ 19፡10፣13፤ ሆሴ. 9፡13)። ታማኝ ተከታዮች የሚጀምሩት እንዳልታመኑ ነው፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ጸጋ በእነርሱ ላይ ተጽዕኖ ይኖረዋል!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የያህዌን ባሕርይ የሚገልጸውን ዋነኛውን ሥነ-መለኮታዊ ጭብጥ ግለጽ፣ መዝ. 92፡2 ላይ።
   ሀ. ቸርነት
   ለ. ታማኝነት
2. ሁለት ወይም ሦስት የዜማ መሣርያዎች ይኖራሉን፣ መዝ. 92፡3 ላይ የተዘረዘሩ?
3. የያህዌ የእጁ ሥራ (ዎች) ምንድናቸው መዝ. 92፡4ለ እና 5ሀ ላይ የተጠቀሱት?
4. መዝ. 92፡7 እና 8 ከሥነ-መለኮት አኳያ እንዴት ይዛመዳሉ?
5. መዝ. 92፡11 ከምን ጋር ይዛመዳል?
6. መዝ. 92፡12-14 ከመዝሙር 1 ጋር እንዴት ይዛመዳል?

# መዝሙር 93
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእት** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የጌታ ግርማ<br><u>ኤምቲ መግቢያየለውም</u> | የጌታ ዘላለማዊ ንግሥና | እግዚአብሔርን እንደ ንጉሥ የማክበር ውዳሴ | እግዚአብሔር ንጉሡ | የእግዚአብሔር ግርማ |
| 93:1-2 | 93:1-2 | 93:1-2 | 93:1-2 | 93:1 |
| | | | | 93:2 |
| | 93:3-4 | 93:3-4 | 93:3-4 | 93:3 |
| 93:3-5 | | | | 93:4 |
| | 93:5 | 93:5 | 93:5 | 93:5 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 93፡1-2**
**[1]እግዚአብሔር ነገሠ፥ ክብርንም ለበሰ**
**እግዚአብሔር ኃይልን ለበሰ፥**
**ታጠቀም ዓለምን እንዳትናወጥ አጸናት።**
**[2]ዙፋንህ ከጥንት ጀምሮ የተዘጋጀ ነው፥**
**አንተም ከዘላለም ነህ።**

**93፡1-2** ይህ አንጓ ያህዌን ይገልጻል፣ በፍጥረት ላይ ገዥ እንደሆነ ንጉሥ (መዝ. 47:2፤ 96:10፤ 97:1፤ 99:1)። የመጀመሪያዎቹ አራት ግሦች፣ የመዝ. 93፡1 የተጠናቀቁ ናቸው።

1. ነገሠ – ቢ.ዲ.ቢ. 573፣ ኬቢ. 590፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 96:10
2. ለበሰ – ቢ.ዲ.ቢ. 527፣ ኬቢ. 519፣ *ቃል* የተጠናቀቀ (ሁለቴ)
3. ታጠቀ – ቢ.ዲ.ቢ. 25፣ ኬቢ. 25፣ *ሂዝፓል* የተጠናቀቀ፣ ራሱን ታጠቀ፣ የያህዌን ሉዓላዊነት እንደሚገልጽ ተገንዘብ

አስገራሚ የሚመስለው የመዝ. 93፡1 ቀጣዮቹ ሁለቱ ግሦች፣ እነርሱም ዓለሙ በጥኑ እንደተመሠረተ የሚናገሩ (ዝከ. 93:2፣ ሂፋል፤ መዝ. 96:10) እና እሱም እንደማይናወጥ፣ ሁለቱም ያልተጠናቀቁ ናቸው፣ በሂደት ላይ የሆነን ድርጊት የሚገልጹ (1 ዜና. 16:30)። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የተጠናቀቁት የሚገልጹት ያለፈ ጊዜን ነው፣ ያልተጠናቀቁት ደግሞ የወቅቱን/የወደፊቱን ጊዜ ነው፣ ግን በዚህ ዘመን ላይ የተወሰነ።

**93፡1** እነዚህ የተጠናቀቁ ግሦች የሚገልጹት የያህዌን ልብሰ-ንግሥና እንደሆነ ተገንዘብ። ልብሱ በዘይቤአዊነት መንገድ የሚያስረግጠው የእርሱን ባሕርይና ኃይል ነው።

1. በግርማ ለብሷል (ቢ.ዲ.ቢ. 145)
2. በኃይሉ ለብሷል (ቢ.ዲ.ቢ. 738)

መዝሙር 104፡1 የሚያስረግጠው "በአስደናቂ" (ቢ.ዲ.ቢ. 217) እና "በግርማ" (ቢ.ዲ.ቢ. 214) መልበሱን ነው። መዝሙር 6፡5-6 የሚያስረግጠው እሱ "በብርታቱ" መታጠቁን ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 150)።

**93፡2** የዘላለማዊው አምላክ ዘላለማዊ ንግሥና (መዝ. 93:5ሐ፤ 45:6፤ 90:2) የተጠበቀ ነው (መዝ. 10:16፤ 29:10፤ 46:10፤ 52:7)! ሁኔታዎች ከፍ ያሉ ሊመስሉ ይችላሉ ነገር ግን እነርሱ ሁሉ ጊዜያዊ ናቸው። አምላካችን ይገዛል (ዳን. 2:44፤ 7:14፣27፤ ሉቃስ 1:33፤ ራዕ. 11:15፣17፤ 19:6)!

***መዝሙር ፡ 93፡3-5***

***[3]አቤቱ፥ ወንዞች ከፍ ከፍ አደረጉ፥***
***ወንዞች ቃሎቻቸውን***
***ከፍ ከፍ አደረጉ።***
***[4]ከብዙ ውኆች ድምፅ***
***ከባሕርም ታላቅ ሞገድ ይልቅ***
***እግዚአብሔር በከፍታው ድንቅ ነው።***
***[5]ምስክርህ እጅግ የታመነ ነው***
***አቤቱ፥ እስከ ረጅም ዘመን ድረስ***
***ለቤትህ ቅድስና ይገባል።***

**93፡3-4** አአመመቅ ይሄንን መዝሙር ወደ ሁለት አንጓዎች ይከፋፍለዋል፣ 93፡1-2 እና 93፡3-5፣ ነገር ግን ሌሎቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ሁሉ፣ የአንጓ ምድቦችን ለማነጻጸር የተጠቀምኩባቸው (አኪጀት፣ አየተመቅ፣ አእቅ፣ አኢመቅ)፣ መዝ. 93:5 እንደ ተለየ የመደምደሚያ ዓረፍተ ነገር ይወስዱታል።

መዝሙር 93፡3-4 የሚናገረው ያህዌ የውኃውን ነውጥ እንደፈጠረውና እንደሚቆጣጠር ነው (መዝ. 74:12-17፤ 89:9-10፤ ኢሳ. 51:9)። መዝ. 93:1 በተጠናቁ እና ባልተጠናቀቁ መካከል ያለውን ተቃርኖ የሚገልጽ እንደሆነ፣ ያለፈውን እና የወቅቱን/የወደፊቱን ድርጊቶች የሚያመለክት፣ የዚህን ዘመን (ዘካ. 14:9)፣ እንዲሁ ደግሞ መዝ. 93፡3። 93፡4 ላይ ምንም ግሥ የለም፣ ግን ደግሞ እሱ ያህዌን እንደ ዘላለማዊ፣ ድል አድራጊ የዩኒቨርስ ንጉሥ ያንጸባርቃል!

**93፡3** ግሡ (ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724) ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ በእያንዳንዱ የቅኔ ስንኝ ላይ። ይህ ቁጥር የሚያንጸባርቀው ለበአል ጥቅም ላይ የዋለውን የቅኔ ስንኝ ነው፣ በራስ ሻምራ ጽሑፎች ላይ የሚገኘውን (ማለትም፣ ዑጋሪታዊ)። የዕብራይስጥ ቋንቋ ዘወትር የጎረቤቶቻቸውን/የማራኪዎቻቸውን ሃይማኖታዊ ምናባዊ ምስያ ወስዶ ለያህዌ፣ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ ተግባራዊ ያደርገዋል!

**93፡4 "*ታላቅ*"** ቅጽሉ (ቢዲቢ 12) ጥቅም ላይ የዋለው የሞገዱን መናወጥ ለመግለጽ ነው (ማለትም፣ የእግዚአብሔርን ጠላቶች፣ በፍጥረት ጊዜ፣ እና በጊዜ ውስጥ፣ እንደ ግብፅና ባቢሎን) ነገር ግን ያህዌ ከፍ ይላል፣ ታላቅ፣ እጅግ ብርቱ ነው፣ ከጠላቶች ሁሉ (መነሻ፣ ጊዜያዊ፣ እና ፍጻሜያዊ)!

**93፡5 "ምስክርነቶች"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 730 III) የሚያንጸባርቀው የያህዌን ራዕይ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ። ያህዌ

1. ያህዌ ራሱ የጸና ዘላለማዊ ንጉሥ ነው
2. ድል አድራጊ ነው፣ በውኃው ነውጥ ላይ
3. ራሱን በሙላት ገልጿል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት) እና የእርሱ ዓላማዎች (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)

▣ **"*ለቤትህ ቅድስና ይገባል*"** ለ"ቅድስና" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ክብር። ኤቢ፣ ቅጽ 17፣ በሚትኬል ዳሆድ (ደግሞም ኒዶቲ፣ ቅጽ 3፣ ቁ. 2፣ ገጽ 2) "ቅድስና" ን ይወስዳል፣ ለሰማያዊ መላእክት ጉባኤ መጠሪያ (መዝ. 29፡1)፣ እናም ስንኙን እንዲህ ለማንበብ
"በመቅደስህ ቅዱሳኑ ላንተ ምስጋና ያቀርባሉ" (ገጽ 339፣ 343)።

▣ "የሚገባ" የሚለው ቃል በሁለት መንገዶች ሊተነተን ይችላል።

1. ግሥ – ቢዲቢ 610፣ ኬቢ 659፣ ፒኤል የተጠናቀቀ (የብኪ ትንታኔ መመሪያ በቤል፣ ባንክ እና ስሚዝ፣ ገጽ 449)
2. ተውሳከ ግሥ — ቢዲቢ 610 (የብኪ የትንታኔ ቁልፍ፣ በኦውንስ፣ ገጽ 425)

"ቤት" የሚያመለክተው የምድረ-በዳውን የማደሪያ ድንኳን ነው፣ ኋላም በኢየሩሳሌም ያለውን መቅደስ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር የሚያመለክተው የፍጥረትን መነሻ ነውን ወይስ ዘጸአትን?

2. መዝሙሩ ከጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ጭብጦች ጋር እንዴት ይዛመዳል
   ሀ. የውኃው ነውጥ
   ለ. እግዚአብሔር እንደ መለኮታዊ ተዋጊ
3. “ምስክርነቶች” ወደ ማን ነው የሚያመለክተው?

# መዝሙር 94
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ ለሕዝቡ እንዲበቀል ጸሎት <u>ኤምቲ መግቢያየለውም</u> | እግዚአብሔር የጻድቅ መጠጊያ | ከክፉ ሰዎች ለመዳን ጸሎት | እግዚአብሔር የሁሉም ዳኛ | የፍትሕ አምላክ |
| 94:1-7 | 94:1-3 | 94:1-3 | 94:1-4 | 94:1-2 |
| | | | | 94:3-4 |
| | 94:4-7 | 94:4-7 | | |
| | | | 94:5-7 | 94:5-6 |
| | | | | 94:7-8 |
| 94:8-11 | 94:8-11 | 94:8-11 | 94:8-11 | |
| | | | | 94:9-11 |
| 94:12-16 | 94:12-15 | 94:12-15 | 94:12-15 | 94:12-13 |
| | | | | 94:14-15 |
| | 94:16-19 | 94:16-23 | 94:16-19 | 94:16-17 |
| 94:17-23 | | | | |
| | | | | 94:18-19 |
| | 94:20-23 | | 94:20-23 | 94:20-21 |
| | | | | 94:22-23 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ተጠሪው በምን ያህል ቁጥር እንደተመለከተ ተገንዘብ፣ አአመመቅ ላይ።
1. አቤቱ ጌታ (ያህዌ)፣ መዝ. 94፡1፣3፣5፣18
2. አምላክ (ኤል) የበቀል (ቢዲቢ 608)፣ መዝ. 94፡1 (ሁለቴ)
3. አቤቱ ጌታ (ያህ)፣ መዝ. 94፡12 (ዝከ. 94፡7)

ለ. ያህዌ ባሕርዩ የተመለከተባቸውን መንገዶች ተገንዘብ፣ በስሙ/በመጠሪያው/ሐረጎች
1. የበቀል አምላክ፣ መዝ. 94፡1
2. የምድር ፈራጅ፣ መዝ. 94፡2
3. የያዕቆብ አምላክ፣ መዝ. 94፡7
4. ጌታ፣ ምሽግ፣ መዝ. 94፡22

5. እግዚአብሔር ዓለት፣ መዝ. 94፡22
6. ጌታ አምላካችን፣ መዝ. 94፡23

ሐ. ይህ መዝሙር ስለ ኪዳን አምላክ ፍትሕ ይጮኻል፣ በዚህ ዓለም ላይ ራሱን እንዲገልጥ። ክፉና ኃጢአተኝነት በአሁኑ ጊዜ በርትቶ ይታያል፣ ነገር ግን በገዛ ራሱ ጊዜ፣ እግዚአብሔር ለጻድቅ ፍትሕን ይሰጣል (ማለትም፣ ፍርድ ይሰጣል)። ይህ መዝሙር የሚያስታውሰኝ የኢየሱስን ምሳሌ ነው፣ ማቴ. 13፡24-30 ላይ ያለውን። በጊዜው፣ በትክክለኛው ጊዜ፣ እግዚአብሔር ያደርጋል፣ ጻድቁን ለመባረክና ለመቀበል፣ ነገር ግን ሐሰተኛ ተከታዮችን ይፈርድባቸዋል፣ ይንቃቸዋልም። በሁለቱም፣ በብኪና በአኪ ሁሉም ተከታዮች በሙሉ ታማኝ ተከታዮች አይደሉም። ሐሰተኞች አሉ (ማቴ. 7፡15-27)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ክህደት።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 94፡1-7**

**[1]እግዚአብሔር የበቀል አምላክ ነው።**
**የበቀል አምላክ ተገለጠ።**
**[2]የምድር ፈራጅ ሆይ፥ ከፍ ከፍ በል**
**ለትዕቢተኞች ፍዳቸውን ክፈላቸው።**
**[3]አቤቱ፥ ኃጢአተኞች እስከ መቼ?**
**ኃጢአተኞች እስከ መቼ ይኰራሉ?**
**[4]ይከራከራሉ፥ ዓመፃንም ይናገራሉ**
**ዓመፃንም የሚያደርጉ ሁሉ ይናገራሉ።**
**[5]አቤቱ፥ ሕዝብን አዋረዱ፥**
**ርስትህንም አስቸገሩ።**
**[6]ባልቴቲቱንና ድሀ አደጉን ገደሉ፥**
**ስደተኛውንም ገደሉ።**
**[7]እግዚአብሔር አያይም፥**
**የያዕቆብ አምላክ አያስተውልም አሉ።**

**94፡1-7** ይህ አንጓ የሚገልጸው የታማኝ ተከታይን ቅሬታ (ተስፋ መቁረጥ) ነው፣ ክፉ ሰዎች እግዚአብሔርን እንደሚያውቁ ሲናገሩ በሚሰማበት/በምትሰማበት ሰዓት (ማለትም፣ ሌሎች የኪዳን ሰዎች፣ ሀብታምና ብርቱዎች የሆኑ)። እነርሱ የሚኖሩት እና የሚያደርጉት ምንም የፍርድ አምላክ እንደሌለ አድርገው ነው (ማለትም፣ ተግባራዊ አምላክ-የለሾች)።

ተገንዘብ

1. ኩሩ ናቸው፣ መዝ. 94፡2ለ
2. ይመካሉ፣ መዝ. 94፡3ለ
3. በትዕቢት ይናገራሉ፣ ("ይከራከራሉ፣" መዝ. 59:7፤ ምሳ. 15:2) መዝ. 94:4a (መዝ. 31:18፤ 75:5)
4. በራሳቸው ይመካሉ፣ መዝ. 94: 4ለ፣ መዝ. 10:3፤ 52:1
5. የእግዚአብሔርን ታማኝ ተከታዮች ያዋርዳሉ፣ መዝ. 94:5ሀ (ማለትም፣ ለተዛባ ፍርድ (ግፍ) ጥቅም ላይ የዋለ፣ ኢዮብ 5:4፤ 22:9፤ መዝ. 10:18፤ 72:4፤ 74:21፤ ምሳ. 22:22፤ ኢሳ. 3:15)
6. የእግዚአብሔርን ርስት ያውካሉ፣ መዝ. 94:5ለ፣ዝከ. 94:14
7. ይገድላሉ (በጥሬው ወይም በዘይቤአዊነት ሊሆን ይችላል፣ ሕጋዊ መብትን ለማጣት)
   ሀ. መበለት
   ለ. መጻተኛ/ስደተኛ
   ሐ. ደሀ አደግ (ዘጸ. 22:21-24፤ ዘዳ. 10:18፤ 14:29፤ 26:12-15)
8. እግዚአብሔር ድርጊቶቻቸውን አይመለከትም ወይም አይገደውም በሚል ያስረግጣሉ፣ መዝ. 94:7 (መዝ. 10:11፤ 59:7፤ 64:5፤ 73:11፤ ኢዮብ 22:13፤ ኢሳ. 29:15፤ 47:10፤ ሕዝ. 8:12፤ ሚል. 2:17)

**94፡1-2** ሦስት የጸሎት ጥያቄዎች (ተተኳሪዎች) አሉ፣ እግዚአብሔር እንዲሠራ የሚለምኑ።

1. በፊትም አብራ – ቢዲቢ 422፣ ኬቢ 424፤ ሂፊል ተተኳሪ፣ መዝ. 80:1፣3፣7፤ እሱም "በሙሴ ባርኮት ላይ ጥቅም ላይ ውሏል" ዘዳ. 33:2 ላይ
2. ተነሥ – ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724፤ ኒፋል ተተኳሪ፤ መዝ. 3:7 እና 7:6 ላይ ማስታወሻውን ተመልከት
3. የሚገባቸውን ክፈል ("መልስ") – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፤ ሂፊል ተተኳሪ፣ ዘዳ. 32:41፣43፤ ኢሳ. 66:15

**94፡1 "በቀል"** ይህ አንስታይ ጾታዊ ቃል (ቢዲቢ 668) የብዙ ቁጥር ነው። የአጽመቅ ጎዳግ እሱን የሚተረጉመው "የበቀል ድርጊት" በሚል ነው። ተባዕታይ መልኩ ዘዳ. 32፡35፣41 ይገኛል። በቀል ያህዌ የሚያደርገው ነው፣ ኪዳኑ በሚጣስበት ጊዜ። አንዳንዴ ከገዛ ራሱ ሕዝብ ጋር ይዛመዳል (በተለይ፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-32፤ ኤር. 5፡9፣29፤ 9፡9፤ ሚክ. 5፡14)፣ አንዳንዴ ከጣዖት አምላኪ ሕዝቦች ጋር (መዝ. 79:10፤ 149:7፤ ኢሳ. 59:18፤ 63:4፤ ናሆ. 1:3)።

**94፡2 "ምድር"** የዕብራይስጡ ቃል ሰፊ የፍች መልክ አለው (ኒዶቲ፣ ቅጽ 1 ገጽ 518-526)። ዐውደ-ጽሑፍ ብቻ ነው ፍችውን መወሰን የሚችለው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር)። እዚህ ሊያመለክት የሚችለው

1. ምድርን ሁሉ (ማለትም፣ ያህዌ የምድር ሁሉ ፈራጅ ነው፣ ዘፍ. 18:25)

2. የተስፋይቱን ምድር፣ እግዚአብሔር የኪዳን አምላክ ነው

ይኸውም አማራጩ ሊወሰን የሚችለው የትኞቹ "ኃጢአተኞች" እንደ ሆኑ ነው፣ የመዝ. 94፡3።

1. እስራኤላውያን ያልሆኑ
2. እስራኤላውያን

እኔ እንደሚመስለኝ አማራጭ ቁ. 2 ከዚህ መዝሙር ጋር በተሻለ የሚገጥም ይመስለኛል፣ ምክንያቱም እነርሱ የሙሴን ትእዛዛት በመጣስ ስለሚከሰሱ (መዝ. 94፡6) እና ከዚያም "በሕዝብ መሐል ያሉ ሰነፎች" በሚል ይጠራሉ (መዝ. 94፡8ሀ)። ያህዌ ጻድቅ ፈራጅ ነው (ዘፍ. 18፡25፤ መሳ. 11:27፤ መዝ. 7:11፤ 50:6፤ 75:7፤ ኢሳ. 33:22)።

**94:3 "እስከ መቼ. . ."** ይህ ፈሊጥ የመጠየቂያ መንገድ ነው

1. እግዚአብሔር ፍትሕን ለምን እንዳላደረገ – መዝ. 6:3፤ 74:10፤ ዕን. 1:2፤ ዘካ. 1:12
2. እግዚአብሔር ሕዝቡን ይቅር ይላልን – መዝ. 13:1፤ 79:5፤ 80:4፤ 90:13፤ ኢሳ. 6:11
3. ኃጢአተኞች ድርጊታቸውን ለምን እንደቀጠሉ – ዘጸ. 10:3፤ 1 ሳሙ. 1:14፤ 1 ነገ. 18:21፤ መዝ. 82:2፤ ኤር. 4:14፤ 12:4፤ ሆሴ. 8:5፤ ዕን. 2:6

ሰዎች የእግዚአብሔርን ሐሳብ፣ ጊዜያት፣ ዓላማ አይገነዘቡም (ኢሳ. 55:9-11)። ይህ ፈሊጥ ይሄንን የእውቀት ማነስ በጥያቄ መልኩ ያቀርበዋል።

## መዝሙር ፡ 94፡8-11

**8የሕዝብ ደንቆሮች ሆይ፥ አስተውሉ**
**ሰነፎችማ መቼ ይጠበባሉ?**
**9ጆሮን የተከለው አይሰማምን?**
**ዓይንን የሠራው አያይምን?**
**10አሕዛብንስ የሚገሥጸው፥**
**ለሰውም እውቀት የሚያስተምረው እርሱ አይዘልፍምን?**
**11የሰዎች አሳብ ከንቱ እንደ ሆነ**
**እግዚአብሔር ያውቃል።**

**94፡8-11** ይህ አንጓ የሚያሳየው እግዚአብሔር አያውቅም ብሎ ማሰብ የቱን ያህል ድንቁርና እንደሆነ ነው (መዝ. 94፡7)።

1. መዝ. 94፡9 የሚያስረግጠው እግዚአብሔር የሰውን አካል ፈጣሪ መሆኑን ነው (ማለትም፣ ጆሮ፣ ዓይኖች)
2. መዝ. 94፡10 የሚያስረግጠው እግዚአብሔር እውነትን እንደሚገልጥ ነው
   ሀ. ለአሕዛብ (መዝ. 94፡10ሀ)
   ለ. ለሰዎች ሁሉ (መዝ. 94፡10ለ)

ማጠቃለያ የሚሆነው ያህዌ የደካማውን ሰው ልጅ ሐሳብ፣ የውስጥ ፍላጎት፣ እና ድርጊት ማወቁን ነው (መዝ. 94:11፤ 11:4፤ 33:13-14፤ 66:7፤ ኢዮብ 11:11፤ 31:4፤ 34:21-23፤ ኤር. 16:17፤ 32:19፤ ሆሴ. 7:2፤ ዕብ. 4:13)። እኛ በፈጣሪያችን ፊት የተከፈትን መጻሕፍት ነን! ያልታመኑ ተከታዮች ሐሳብ (መዝ. 94:15) ከንቱ ነው (ቢዲቢ 210 1፣ መዝ. 94:4-7፣8)።

**94፡8 "እናንተ ደንቆሮዎች"** ይህ ቃል የድርጊት አንቀጽ ነው (ቢዲቢ 129፣ ኬቢ 146)፣ እሱም ከእንስሳ ወይም ከአውሬ ሥር የመጣ (ቢዲቢ 129)። ስሙ ለእንስሳ በትይዩነት ጥቅም ላይ ይውላል፣ መዝ. 73፡22 ላይ። እሱም የሚጠቅሰው እንደ እንስሳ ለሚያደርገው ሰው ነው፣ ያለ ሞራላዊ ከልከላ። እሱም ዘወትር የሚያመለክተው ጣዖት አምላኪዎችን ነው (ማለትም፣ ኤር. 10፡8)።

▣ ***"መገሥጽ"*** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 406፣ ኬቢ 410፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ) የፍርድ ቤት ቃል ነው። ይህ ሙሉ መዝሙር ለአለቆች ነው የተመለከተው፣ ያህዌን እንዲያንጸባርቁ፣ ነገር ግን በአስደንጋጭ መልኩ የወደቀውን ዓለም ያንጸባርቃሉ።

ግልጽ የሆነ የቃላት መቀያየር (ጨዋታ) ይኖራል፣ በ "ዘለፋ" (ቢዲቢ 415) እና "መገሥጽ" (ቢዲቢ 406) መካከል፣ ይኸውም ዘወትር የሚከሰት (መዝ. 6:1፤ 38:1፤ ምሳ. 9:7፤ ኤር. 2:19) እናም ሰዎች ለእርሱ መገለጥ ኃላፊነት እንዳለባቸው ያስይዛል።

**94፡11** ጳውሎስ ይሄንን ቁጥር ጠቅሷል፣ 1 ቆሮ. 3፡20 ላይ፣ ከLXX በእርሱ "የጠቢብ" ማብራሪያ ላይ፣ በቆሮንቶስ ላለች ቤተ-ክርስቲያን። የሰው ጥበብ ከንቱ፣ የማይረባ ነው!

ያህዌ ራሱን በሁለት መንገዶች ገልጧል።

1. ተፈጥሯዊ መገለጥ – መዝ. 19:1-6፤ ሮሜ. 1:19-20
2. ልዩ መገለጥ – መዝ. 19:7-11፤ 119

## መዝሙር ፡ 94፡12-16

**12-13ለኃጢአተኛ ጉድጓድ እስኪቈፈር ድረስ**
**ከክፉዎች ዘመናት ይወገድ ዘንድ፥**
**አቤቱ፥ አንተ የገሠጽኸው**
**ሕግህንም ያስተማርኸው ሰው ምስጉን ነው።**
**14እግዚአብሔር ሕዝቡን አይጥልምና፥**
**ርስቱንም አይተውምና**
**15ፍርድ ወደ ጽድቅ እስኪመለስ ድረስ**
**ልበ ቅኖችም ሁሉ ይከተሉአታል።**

[16]በክፉዎች ላይ ለእኔ የሚቆም ማን ነው?
ዓመፃን በሚያደርጉ ላይ ለእኔ የሚከራከር ማን ነው?

**94፡12-16** መዝ. 94፡3-7 እና 8-9 የኃጢአተኛን ቃል እና ድርጊት እንደሚገልጹ ሁሉ፣ ይህ አንጓ ከታማኝ ተከታዮች ጋር ይያያዛል።

1. እነርሱ ተባርከዋል (የጥበባዊ ሥነ-ጽሑፍ ባሕርያዊ ቃል፣ ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 1፡1 ላይ) በያህዌ ተግሣጽ እንኳ ቢሆን (ዕብ. 12፡5-13)፤ መዝ. 94፡12
2. እነርሱ ተባርከዋል፣ ከያህዌ ሕግ በመማር (ማለትም፣ የተለየ መገለጥ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር መገለጥ እና ልዩ ርዕስ፡ ባርኮት [ብኪ])፣ መዝ. 94፡12
3. ዕረፍታቸው የተረጋገጠ ነው (ማለትም፣ ውስጣዊ ሰላም፣ ቢዲቢ 1052) ከክፉ ቀናት፣ ክፉዎች በገዛ ራሳቸው ተንኮል እስከሚያዙ ድረስ፣ መዝ. 94፡12
4. እነርሱ በያህዌ የተተዉ አይደሉም፣ (መዝ. 37፡28፤ 1 ሳሙ. 12፡22፤ሰቆ. 3፡31)፣ መዝ. 94፡14
5. እነርሱ ፍትሕን ይቀበላሉ በእርሱም ይራመዳሉ፣ መዝ. 94፡15

**94፡16** ይህ ቁጥር የዚህን መዝሙር ግለሰባዊ ጠባይ ያሳያል፣ ነገር ግን ደግሞ ለመዝሙረኛው ወዳጆች ልመና ነው፣ እሱን እንዲረዱትና እንዲደግፉት (በፍርድ ችሎት ሊሆን ይችላል)። እሱም ለንጉሥ በቀላሉ ሊሆን ይችላል! በዚህ የንጉሣዊነት ይሁንታ ላይ የእኔ ችግር የሚሆነው፣ ንጉሥ ቢሆን ኖሮ፣ ክፉዎቹን አለቆች ለምን አይተካቸውም ነበር?

**መዝሙር ፡ 94፡17- 23**

**[17]እግዚአብሔር የረዳኝ ባይሆን**
**ነፍሴ ለጥቂት ጊዜ በሲኦል ባደረች ነበር።**
**[18]እግሮቼ ተሰናከሉ ባልሁ ጊዜ፥**
**አቤቱ፥ ምሕረትህ ረዳኝ።**
**[19]አቤቱ፥ ለልቤ እንደ መከራዋ ብዛት**
**ማጽናናትህ ነፍሴን ደስ አሰኛት።**
**[20]በሕግ ላይ ዓመፅን የሚሠራ**
**የዓመፅ ዙፋን ከአንተ ጋር አንድ ይሆናልን?**
**[21]የጻድቅን ነፍስ ያደቡባታል፥**
**በንጹሕ ደምም ይፈርዳሉ።**
**[22]እግዚአብሔር መጠጊያ ሆነኝ፥**
**አምላኬ የተስፋዬም ረዳት ነው።**
**[23]እንደ በደላቸውም እንደ ክፋታቸውም**
**ፍዳቸውን ይከፍላቸዋል፥**
**አምላካችን እግዚአብሔርም ያጠፉቸዋል።**

**94፡17-23** ይህ አንጓ ተለጣጣቂ የሆኑ መግለጫዎችና ውጤቶች ነው።

1. ያህዌ ረዳት ሆኖኛል፣ ስለዚህ አልሞትም፣ መዝ. 94፡17
2. ተሰናከልሁ ባልሁ ጊዜ፣ የእግዚአብሔር የኪዳን ፍቅር አጸናኝ፣ መዝ. 94፡18
3. በተጨነቅሁ ጊዜ፣ ያህዌ ነፍሴን አጽናና፣ መዝ. 94፡19
4. ያህዌ ምሽጉና የመጠጊያው ዓለት ሆኖለታል፣ መዝ. 94፡22 (ዘዳ. 32፡15፤ መዝ. 18፡1-2፤ 62፡6-7፤ መዝ. 5፡11)
5. እግዚአብሔር መልሶ ያመጣባቸዋል (እንደ 94፡2 ግሥ ተመሳሳይ) በኃጢአተኞች ላይ የገዛ ራሳቸውን ክፉ፣ መዝ. 94፡20-21፤23 (ቁ. 4 እና 5 አንድ ላይ ይሄዳሉ)

**94፡17**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"የጸጥታ ማደሪያ ስፍራ"** |
| **አኪጀት፣ ጀፒኤስአኤ** | **"በጸጥታ"** |
| **አየተመቅ፣ አእቅ** | **"በጸጥታ ምድር"** |
| **አኢመቅ** | **"በጸጥታ"** |
| **LXX** | **"በሲኦል"** |

ይህ የሞት ምናብ ነው (መዝ. 115፡17፤ ማለትም፣ ሲኦል፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሲኦል)። ሞት ይታይ የነበረው ንቁነት እንዳለው ግን ጸጥታማ ነው (መዝ. 6፡5)።

**94፡18 "እግሮቼ ተሰናከሉ"** በመጽሐፍ ቅዱስ የሰው ሕይወት ባሕርይ የቀረበው እንደ ፈለግ/መንገድ/ጎዳና ነው። በአሉታዊነት መንገዱ የለዘበ፣ የተካከለ፣ ቀና ነው፣ ያለ ማሰናከያ። በአሉታዊ መንገዱ ጨለማ፣ የተበላሸ፣ የሚያዳልጥ ነው፣ በብዙ ማሰናከያ።

**94:20**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"የጥፋት ዙፋን"** |
| **አኪጀት** | **"የዓመጽ ዙፋን"** |
| **አየተመቅ** | **"ኃጢአተኛ አለቆች"** |

**አእቅ** **"ብልሹ ፈራጆች"**
**አኢመቅ** **"የጥፋት ችሎት"**
**ጀፒኤስአኤ** **"የዓመጸ ወንበር"**
**LXX** **"የዓመጸ ዙፋን"**

ኤምቲ ቢዲቢ 490 አወቃቀር አለው፣ ቢዲቢ 217። ቢዲቢ 490 የሚለው ወንበር ወይም የሥልጣን ስፍራ ወይም ለንጉሥ፣ ለሊቀ ካህን፣ ወይም ለገዥ የሆነ ክብር። ቢዲቢ 217፣ ኬቢ 241 የሚለው "ሥልጣን" "ድንቅ፣" ወይም "ግርማ" ነው። ይህ መዝሙር የፍርድ-ቤት ትዕይንት ነው፤ ያህዌ የምድር ፈራጅ ነው (መዝ. 94፡1-2)። መዝሙር 94፡16 ደግሞ የፍርድ-ቤት ትዕይንትን ያንጸባርቃል። ቁጥር 20 የሚያመለክተው ስለ ኃጢአተኛ መሪዎች ነው (ማለትም፣ ፈራጆች)። ያህዌ ከኃጢአተኛ መሪዎች ጋር መተባበር አይችልም (መዝ. 94፡10-21)። ዙፋኑ፣ መቅደሱ፣ እና ችሎቱ የያህዌን ባሕርይ ማንጸባረቅ ይኖርበታል። እነርሱ በማያደርጉበት ጊዜ፣ ይኸውም ተዘውትሮ የተደረገ ጉዳይ፣ ያህዌ ራሱ ብቻ የደኅንነት ስፍራ ነው!

መዝሙር 94፡20 ማረጋገጫነቱ፣ ያህዌ በተበላሸ የሕግ ሥርዓት ላይ ምንም ክፍል እንደሌለው ነው። እግዚአብሔር ብርሃን ነው፣ በእርሱም ዘንድ ጨለማ የለም (1 ዮሐንስ 1፡50 እና መለወጥ የሌለበት፣ ሚል. 3፡6፤ ያዕቆብ 1፡17)።

▣ **"በሕግ ላይ ዓመፅን የሚሠራ"** እዚህጋ ያለው አንቀጽ ቢዲቢ 427፣ ኬቢ 428፣ *ቃል*። እሱም 94፡9 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ለያህዌ የፈጠራ ተግባር፣ የሰውን ዓይን በማበጀት። እንዴት ያለው ተቃርኖ ነው! ሰዎች ተንኮልን ይፈጥራሉ፤ ያህዌ ሰዎችን ፈጥሯል!

**94፡21 "ሕይወት"** ይህ በጥሬው ኔፊሽ ነው (ቢዲቢ 659)። ማስታወሻ ተመልከት፣ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር፣ መዝ. 3፡2 ላይ።

**94፡23** አአመመቅ "ጸጥታ" የሚል አለው፣ በሁለቱም መዝ. 94፡17 እና 23፣ ነገር ግን ኤምቲ ላይ የተለያዩ ቃላት ናቸው። መዝ. 94፡23 ላይ (ሁለቴ) ያለው "እግዚአብሔር ያጠፋቸዋል" የሚል ነው (ቢዲቢ 856፣ ኬቢ 1035፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ)። እሱም ሁለት ጊዜ ለአጽንዖት ተደግሟል።

ለሰዋሰዋዊ ማስታወሻ ያህል። ሁሉም ሦስቱም ግሦች መዝ. 94፡22 ላይ ያሉት ያልተጠናቀቁ እንደሆኑ ተገንዘብ፣ ነገር ግን እነርሱ ወደ እንግሊዝኛ የተተረጎሙት እንደ ሀላፊና ትንቢት ግሦች ነው (አየተመት፣ አእት ሦስቱም ሁሉም የትንቢት ጊዜ ናቸው)። ዐውደ-ጽሑፍ ብቻ ነው የዕብራይስጥን ግሦች የጊዜ ይዘት የሚወስነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በመዝ. 94፡1-2 እና 94፡3 መካከል ያለው ሥነ-መለኮታዊ ችግር ምንድነው?
2. "ኃጢአተኞች" እነማናቸው፣ መዝ. 94፡3 ላይ?
3. መዝሙር 94፡6 እንዴት ዘዳግምን ይመስላል?
4. መዝ. 94፡10 የሚያመለክተው ሰዎችን ሁሉ ነው ወይስ እስራኤልን?
5. መዝ. 94፡16 የፍርድ-ቤት ትዕይንት ነውን?
6. መዝ. 94፡16-23 ላይ ምን ያህል አንጓዎች አሉ?

# መዝሙር 95
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ምስጋና ለጌታ፣ እና ማስጠንቀቂያ ባለማመን<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | የአምልኮና የመታዘዝ ጥሪ | የእግዚአብሔር ንግሥና የአምልኮ ሥርዓት | የምስጋና መዝሙር | የምስጋና ግብዣ |
| 95:1-5 | 95:1-5 | 95:1-5 | 95:1-5 | 95:1-2 |
| | | | | 95:3-5 |
| 95:6-7 | 95:6-7ለ | 95:6-7ለ | 95:6-7ለ | 95:6-7ለ |
| | 95:7c-11 | 95:7ሐ-11 | 95:7ሐ-11 | 95:7ሐ-9 |
| 95:8-11 | | | | 95:10-11 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ሦስተኛው አንቀጽ

4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 95፡1-5**
**1ኑ፥ በእግዚአብሔር ደስ ይበለን**
**ለአምላክ ለመድኃኒታችን እልል እንበል።**
**2በምስጋና ወደ ፊቱ እንድረስ፥**
**በዝማሬም ለእርሱ እልል እንበል**
**3እግዚአብሔር ታላቅ አምላክ ነውና፥**
**በአማልክትም ሁሉ ላይ ታላቅ ንጉሥ ነውና።**
**4እግዚአብሔር ሕዝቡን አይጥላቸውም**
**የምድር ዳርቻዎችም በእጁ ውስጥ ናቸው፥**
**የተራሮች ከፍታዎች የእርሱ ናቸው።**
**5ባሕር የእርሱ ናት እርሱም አደረጋት፥**
**የብስንም እጆቹ ሠሩአት።**

**95፡1-5** ይህ አንጓ ጥሪ ነው (ተተኳሪ እና 4 ተጓዳኝ) ያህዌን እንደ ንጉሥና ፈጣሪ ለማምለክ።
1. ኑ – ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. በደስታ እንዘምር – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ *ፒል ተጓዳኝ*፣ መዝ. 66:1፤ 81:1
3. በደስታ እልል እንበል – ቢዲቢ 929፣ ኬቢ 1206፣ *ሂፊል ተጓዳኝ*
4. ወደ ፊቱ እንድረስ (ማለትም፣ መቅደስ) – ቢዲቢ 869፣ ኬቢ 1068፣ *ፒል ተጓዳኝ*
5. በደስታ እልል እንበል – ቢዲቢ 929፣ ኬቢ 1206፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*

እነዚህ ጥሪዎች ናቸው፣ በመቅደስ ለማምለክ። አምልኮ ለያህዌ የሚገባው ስለሆነ
1. የደኅንነታችን ዓለት — ይህ እና ተመሳሳይ መግለጫዎች እንደ መጣሪያ ሆነው ያገለግላሉ፣ ባብዛኛው መዝሙር እና ኢሳይያስ ላይ
   ሀ. እግዚአብሔር ደኅንነቴ ነው – መዝ. 88፡1፤ (መዝ. 24፡5፤ 27፡9)
   ለ. አዳኜ እና አምላኬ – መዝ. 42፡5-6፣11፤ 43፡5
   ሐ. የደኅንነቴ ዓለት – 2 ሳሙ. 22፡47፤ መዝ. 62፡2፣7፤ 89፡26፤ 95፡1
   መ. እግዚአብሔር አዳኛችን –መዝ. 65፡5፤ 68፡19፤ 85፡4፤ 149፡4 (ኒዶቴ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ. 561 ተመልከት)
2. ታላቅ አምላክ (ኤል)፣ መዝ. 48፡1፤ 96፡4፤ 135፡5፤ 145፡3
3. ታላቅ ንጉሥ (1 ሳም. 8፡7)
4. ከአማልክት ሁሉ በላይ (ዘጸ. 18፡11፤ መዝ. 96፡4፤ 97፡9፤ 135፡5፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: አሀዳዊነት፤ ይህ የኤሎሂም አጠቃቀም ነው፣ እሱም የብዙ ቁጥሩን መልክ የያዘ፣ ዘጸ. 3፡6፤ 20፡3፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች

**95፡1 "የደኅንነታችን ዓለት"** የእስራኤል አምላክ በዓለት ምስያ መቅረቡ ተደጋጋሚ ነው (ዘዳ. 32፡4፣ 15፣18፣30፣31፤ 1 ሳሙ. 2፡2፤ 2 ሳሙ. 22፡3፣ 32፣47፤ 23፡3፤ መዝ. 18፡2፣31፣46፤ 28፡1፤ 61፡2፣7፤ 78፡35፤ 89፡26፤ 92፡15፤ 94፡22)። እሱም እንደ ብርቱ፣ ዘላለማዊ፣ የጸና፣ እና የደኅንነትና የተጠበቀ ስፍራ አድርጎ ይገልጸዋል!

**95፡4 "የምድር ዳርቻዎች"** "ዳርቻዎች" የሚለው ቃል (חקר ፣ ቢዲቢ 350፣ ኬቢ 571) እዚህ*ጋ* ብቻ ነው የሚገኘው። እሱም ከ "መሬት" *ጋ*ር መዋቅራዊ ግንኙነት አለው፣ እንዲሁም "ከተራሮች ጫፎች" *ጋ*ር ትይዩነት አለው። ይህ በግልጽ እንደሚታየው የሥጋዊ ፍጥረት ቅኔአዊ ስንኝ ነው (ማለትም፣ መዝ. 95፡4-5)፣ ይኸውም ያህዌ ሁሉንም የምድርን ሥጋዊ ገጽታዎች እንደ ፈጠረ የሚገልጽ። እሱ የሥጋዊ አካል ንጉሥና ፈጣሪ ነው (ሌሎች የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አማልክት ወይም አፈ-ታሪኮች ሳይሆኑ)። ዛሬ ጥያቄ የሚሆነው፣ "ሥጋዊ ፍጥረት ነሲባዊ ነው ወይስ ዓላማዊ?" የሚለው ነው። አማኞች "ዓላማዊ" እንደ ሆነ ያስረግጣሉ!

አንድ ተጨማሪ ሐሳብ። ቀደም ባለው አንቀጽ ላይ መዝ. 95፡4ን ከ95፡3ሀ *ጋ*ር አዛምጃለሁ። እሱን ከ95፡3ለ *ጋ*ር ማዛመድ ይቻላል። እንደዚያ ከሆነ፣ "ዳርቻዎች" እና "ተራሮች" ስፍራዎች ሊሆኑ ይችላሉ ጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አማልክት ይኖሩበታል ብለው የሚያስቡት። በእነዚህ ስፍራዎች ላይ "አማልክት" (ኤሎሂም) ሳይሆኑ ያህዌ *ኤሎሂም* የፍጥረት አምላክ (ዘፍጥረት 1-2) የሚገዛው!

▣ **"እጅ"** "እጅ" እንደገና መዝሙር 95፡5 ላይ መከሰቱን ተመልከት። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ።

**95፡5 "ባሕር… እርሱም አደረጋት"** አስገራሚ የሚሆነው፣ ዘፍጥረት 1 ላይ ብቸኛው ምድራዊ ነገር ወደ ሕላዌ መምጣቱ ያልተጠቀሰው ውኃ ነበር (ጨዋማ እና ንጹሕ)። እግዚአብሔር ውኃን ከፋፍሏል፣ እናም ዳርቻዎቻቸውን ተቆጣጥሯል፣ ነገር ግን እንደ ፈጠራቸው አልተባለም፣ እንዲሁ ደግሞ፣ መዝሙር 104።

ሆኖም፣ እርሱ ሁሉንም ነገር ለመፍጠሩ፣ "ባሕሮችንም" ጨምሮ፣ ያለው ሥነ-መለኮታዊ ማስረገጫ፣ ነህ. 9፡6፤ መዝ. 95፡5፤ 146፡6፤ ዮናስ 1፡9 ላይ ይገኛል።

ደግሞም መዝ. 95፡5ለ የሚያስረግጠው እግዚአብሔር እንደሠራ ነው (ቢዲቢ 427፣ ኬቢ 468፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) የብሱን (ደረቁን መሬት)። ዘፍጥረት 1፡9-10 የሚያስረግጠው እሱም በንግግር ቃሉ እንደሆነ። ይህም የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ምናባዊ ምስያ እንደሆነ አስታውስ። በቅኔአዊ ስንኞች ላይ ሥነ-መለኮትን መፍጠር አይኖርብንም። እኔ እንደማስበው ዘፍጥረት 1-11 ሁለቱንም ታሪካዊና ጥሬአዊ እንደሆነ ነው። እባክዎን የሥነ-ትርጓሜውን ሐተታ ይመልከቱ፣ በዘፍጥረት www.freebiblecommentary.org. ምዕራባዊ፣ ዘመናዊ ሰዎች እጅግ ጥሬአዊና አድቅቀው የሚከፋፍሉ ናቸው፣ ቅዱስ ቃሉን ሲይዙ (ድረ-ገጽ ተመልከት በመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ላይ)።

### መዝሙር ፡ 95፡6-7

**[6]ኑ፥ እንስገድ ለእርሱም እንገዛ**
**በእርሱ ባደረገን በእግዚአብሔር ፊት እንበርከክ**
**[7]እርሱ አምላካችን ነውና፥**
**እኛ የማሰማርያው ሕዝብ**
**የእጁም በጎች ነንና።**

**95፡6-11** ይህ አንጓ የሚመለከተው የኪዳን ሕዝቦችን ነው፣ ለእነርሱም ጥሪ የሚያደርገው
1. ለአምልኮ (መዝ. 95፡6)
   ሀ. ኑ ("ግቡ"፤ ከመዝ. 95፡1 የተለየ ቃል፣ ነገር ግን ትይዩ) – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል ተተኳሪ*
   ለ. እናምልክ – ቢዲቢ 1005፣ ኬቢ 295፣ *ሂሽታፌል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   ሐ. እንስገድ – ቢዲቢ 502፣ ኬቢ 499፣ *ቃል ተጓዳኝ*
   መ. እንበርከክ – ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ *ቃል ተጓዳኝ*
2. በእምነት ምላሽ እንስጥ (መዝ. 95፡7)
3. ልባችንን አናደንድን፣ እንዳለፉት ሰዎች (ማለትም፣ በምድረ-በዳ የእንክርት ጊዜ፣ መዝ. 95፡8-11)

**95፡6 "ያደረገን"** ዘፍጥረት 2፡7 የአዳምን ልዩ አፈጣጠር ያሳያል። እንሰሳትም ደግሞ ከምድር ይፈጠሩ ዘንስ ተብሏል፣ ዘፍ. 2፡19 ላይ (ተመሳሳይ ግሥ፣ ቢዲቢ 427፣ ኬቢ 428)።

መዝ. 139፡13-16 ላይ ("ማበጀት፣" ቢዲቢ 697፣ ኬቢ 754) እና ኢዮብ 31፡15 ላይ ("መሥራት፣" ቢዲቢ 793፣ ኬቢ 889፣ ደግሞም መዝ. 139፡15) እግዚአብሔር እያንዳንዱን ሰው በማኅፀን ሠርቶታል። የተለያየ መሆኑ ጥሬአዊ ነው፣ ነገር ግን እውነታው እግዚአብሔር መፍጠሩ/ማበጀቱ ነው (መዝ. 100፡3፤ 149፡2፤ ኢሳ. 17፡7፤ ሆሴ. 8፡14)። ሰዎች የእግዚአብሔር ልዩ ፍጡር ናቸው፣ በመልኩና ባምሳሉ (ዘፍ. 1፡26-27) ለኅብረታዊ ዓላማ! ይሄንን ማጣት ማለት የሰው ልጅን ዋጋ እና ክብር ማጣት ማለት ነው (መዝሙር 8)።

**95፡7ሐ-11** አስገራሚ የሚሆነው ብኪ የምድረ-በዳውን የመንከራተት ጊዜ እንዴት አድርጎ በተለያየ መንገድ መግለጹ ነው።
1. በአዎንታዊ
   ሀ. ዘዳ. 32፡10-14
   ለ. ኤርምያስ 2
   ሐ. ሆሴዕ 2:15፤ 9:10፤ 11:1-2
2. በአሉታዊ
   ሀ. ዘኍ. 14:1-17
   ለ. መዝ. 95:8-11
   ሐ. ሕዝቅኤል 23

ይህ የሕይወታችን ሁሉ ግራ አጋቢ ነው። ማንም ፍጹም አይደለም። መልካም ቀናት እና ክፉ ቀናት አሉ፣ የብርታት እና የድካም ስፍራዎች አሉ። እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን፣ ስለማይለወጥ፣ መሐሪ ባሕርዩ፣ ስለ አዲስ ኪዳን (ማለትም፣ ኤር. 31-34)፣ እና ስለ መሲሑ (ማለትም፣ የአኪ ራዕይ)።

**95፡7** እግዚአብሔር እንደ እረኛ እና የእርሱም ሕዝብ እንደ በጎች የተለመደ የብኪ ምናባዊ ምስያ ነው (መዝ. 23 ላይ ማስታወሻ ተመልከት)።

በእረኛና በበጎች መካከል ያለው ቅርብ ወዳጅነት ጠንካራና ቋሚ ነው። የበጎች እረኛቸውን ያለመስማት አስቀያሚና አደገኛ ነው! ውድቀቱ ሁላችንንም ጎድቶናል!
1. አልሰሙም (መዝ. 95:7ሐ፣ ዕብ. 3:7-11፣15፤ 4:7 ላይ የተጠቀሰ)
2. ልባቸውን አደነደኑ
   ሀ. መሪባ –ዘጸ. 17:7፤ ዘኍ. 20:13
   ለ. ማሳህ –ዘጸ. 17:7፤ ዘዳ. 6:16
3. እግዚአብሔርን ፈተኑት –ዘኍ. 14:22

በርካቶቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች አዲስ አንቀጽ ይጀምራሉ፣ መዝ. 95:7ሐ ላይ፣ ምክንያቱም እዚህ ነጥብ ላይ፣ በመዝሙሩ ያህዌ ነው የሚናገረው (መዝ. 95:7ሐ-11)።

**መዝሙር ፡ 95፡8-11**

**8 በምድረ በዳ እንደ ተፈታተኑት እንዳስቈጡት ጊዜ፥**
**ዛሬ ድምፁን ብትሰሙ ልባችሁን አታጽኑ።**
**9 የተፈታተኑኝ አባቶቻችሁ**
**ፈተኑኝ ሥራዬንም አዩ።**
**10 ያችን ትውልድ አርባ ዓመት ተቈጥቻት ነበር።**
**ሁልጊዜ ልባቸው ይስታል፥**
**እነርሱም መንገዴን አላወቁም አልሁ።**
**11 ወደ ዕረፍቴም እንዳይገቡ**
**በቍጣዬ ማልሁ።**

**95፡9** እስራኤል በዘጸአት የተለማመደው ተአምራቶች እና በምድረ-በዳ ያየው ጥበቃና መጋቢነት አለማመናቸውን እና የመታመን እጥረታቸውን እጅግ የከፋ አድርጎታል።

**95፡10 "አርባ ዓመት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተምሳሊታዊ ቁጥሮች በቅዱስ ቃሉ። አርባ ዘወትር ክበባዊ ቁጥር ነው።

**95፡11 "በቁጣዬ ማልሁ"** ሰዎች የዚህን ዓለም ቃላት ለመጠቀም ይገደዳሉ፣ እግዚአብሔርን፣ የሱን ሐሳብ፣ ስሜቶቹን፣ እና ድርጊቶቹን ለመግለጽ፣ ግን እነርሱ ዘይቤአዊ ብቻ ናቸው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰውኛ ሲገለጽ)።

እነዚህ ዘይቤዎች እውነት ናቸው ነገር ግን ሁሉንም ያካተቱ አይደሉም። እነርሱ በእውነተኝነት ያስረግጣሉ፣ የአለማመንንና ዓመጸኝነትን ውጤት እውነታ፣ በሁለቱም በጊዜና በዳርቻ (ከዛም ባለፈ)! ይህ የእስራኤል ትውልድ፣ አሮንንና ሙሴንን ጨምሮ ወደ ከነአን አልገቡም (ዕብራውያን 3-4፤ ዘዳ. 3:20፤ 12:9፤ 25:19)።

ይህ መዝሙረኛ ለያህዌ አምልኮን፣ መታመንን፣ እና መታዘዝን ያቀርባል። ለእርሱ ምስጋናና እምነት ይገባዋል!

ዕብራውያን 3-4 ይሄንን ጽሑፍ ይጠቀማል፣ ሦስቱን "የዕረፍት" ስሜቶች ለማስረገጥ።
1. ሰላም ከእግዚአብሔር ጋር
2. የተስፋይቱ ምድር
3. ሰማይ

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "የመዳናችን ዓለት" የሚለውን ሐረግ ታሳቢ መነሻ አብራራ።
2. መዝ. 95፡4 ከመዝ. 95፡3ለ እንዴት ይዛመዳል?
3. "ባሕር" በኤሎሂም እንደተፈጠረ ዘፍጥረት 1 ላይ ለምን አልተጠቀሰም?
4. የመዝ. 95፡7ሐን ታሳቢ አንድምታ (ማለትም፣ "እንደ") አብራራ።
5. እግዚአብሔርን እንዴት እንፈትነዋለን/እንፈትሸዋለን?
6. "ዕረፍት" የሚለውን ቃል አጠቃቀም በዕብራውያን 3-4 ላይ፣ ይሄንን መዝሙር የጠቀሰውን አብራራ።

# መዝሙር 96
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታን ጻድቁን ፈራጅ የማምለክ ጥሪ<br>ኤምቲ መግቢያየለውም | በፍርድ ለሚመጣው አምላክ የምስጋና መዝሙር | የእግዚአብሔርን ንግሥና ለማክበር ውዳሴ | እግዚአብሔር ሉዓላዊው አምላክ | ያህዌ፣ ንጉሥና ፈራጅ |
| 96:1-6 | 96:1-3 | 96:1-6 | 96:1-3 | 96:1-2ሀ |
| | | | | 96:2ለ-3 |
| | 96:4-6 | | 96:4-6 | 96:4-5ሀ |
| | | | | 96:5b-6 |
| 96:7-10 | 96:7-9 | 96:7-9 | 96:7-9 | 96:7-8ሀ |
| | | | | 96:8ለ-9 |
| | 96:10 | 96:10-13 | 96:10-13 | 96:10 |
| 96:11-13 | 96:11-13 | | | 96:11-12 |
| | | | | 96:13 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ እጅግ አስደሳችና ጠቃሚ መዝሙር ነው። እሱም የአሀዳዊነትን ሁለንተናዊ አንድምታ ያዳብራል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት)። እሱም ደግሞ የአሀዳዊነትን ሥነ-ምግባራዊ አንድምታ ያዳብራል (ማለትም፣ የፍትሕና የጽድቅ ዓለም)። ይህም የፍጻሜያዊ ዘመን የፍርድ ቤት ትዕይንትን ሊያንጸባርቅ ይችላል፣ እንደ ማቴ. 25:31-46 እና ራዕ. 20:11-15።

ለ. ይህ መዝሙር የፍጻሜ ዘመን ማጣቀሻ አለው። ምድር ሁሉ (መዝ. 96፡1፣3፣7፣9፣10፣13) አንድ ቀን ለእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እውቅና ይሰጣል፤ "ያህዌ ይገዛል" (ኢሳ. 52፡7)!

ሐ. ይህ መዝሙር 1 ዜና. 16፡23-33 ላይ ተጠቅሷል፣ እንድ ትልቅ መዝሙር(ራት) ክፍል [ማለትም፣ መዝ. 96፡1-36] ዳዊት ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ከማምጣቱ ጋር በተያያዘ። ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ዳዊት (LXX)፣ አሳፍ፣ ወይም የእርሱ ቤተሰብ ጸሐፊው ሊሆኑ ይችላሉ። ኤምቲ ምንም የመግቢያ ሐረግ የለውም።

መ. ይህ መዝሙር ሁለንተናዊ የአምልኮ መቼትን ያንጸባርቃል፣ የአንዱ አምላክ አስተዋጽዖና ድርጊት በሰዎች ሁሉ የሚመሰገንበት (ማለትም፣ ንጉሥና ፈራጅ)! ይህም የመቅደሱ ውጫዊ ስፍራ ተግባር የሆነ (1 ነገ. 8:43፣60፤ ኢሳ. 56:7፣ማቴ. 21:13፤ ማርቆስ 11:17)።

ሠ. ይህ መዝሙር ከያህዌ በርካታ መንብርኖቶች ጋር ለመግጠም ባጠቃላይ በቂ ነው። "አዲሱ መዝሙር" ስለ እግዚአብሔር ቀጣይነት ያለው የማዳን ድርጊት ይናገራል፣ ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ለሥጋ ሁሉ እንጂ። ማዳኑ ሁለንተናዊ ነው (ልዩ ርዕስ፡ የያህዌ ዘላለማዊ የማዳን ዕቅድ)።

ረ. ምንም እንኳ የተለየ መሲሐዊ ጠቃሽ ባይኖርም፣ ቀጣይነት ካለው መገለጥ የተነሣ ይህን ሁለንተናዊ መዋጀት እና ግዛት መቀዳጃው አገባብ መሲሑ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሲሕ፣ ማለትም፣ ኢሳይያስ 6፤ 9፤ ዳንኤል 7፤ ሚክያስ 5)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 96፡1-6**

**1ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋናን አመስግኑ**
**ምድር ሁሉ፥ እግዚአብሔርን አመስግኑ።**
**2እግዚአብሔርን አመስግኑ ስሙንም ባርኩ፥**
**ዕለት ዕለትም ማዳኑን አውሩ።**
**3ክብሩን ለአሕዛብ**
**ተኣምራቱንም ለወገኖች ሁሉ ንገሩ**
**4እግዚአብሔር ታላቅ ምስጋናውም ብዙ ነውና፥**
**በአማልክትም ሁሉ ላይ የተፈራ ነውና።**
**5የአሕዛብ አማልክት ሁሉ ኢጋንንት ናቸውና**
**እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ።**
**6ምስጋናና ውበት በፊቱ፥**
**ቅዱስነትና ግርማ በመቅደሱ ውስጥ ናቸው።**

**96፡1 "ለእግዚአብሔር ዘምሩ"** ይህ ተተኳሪ ነው፣ ሦስት ጊዜ ለአጽንዖት የተደገመ (ደግሞም መዝ. 96፡7-8 ላይ፤ ይህም በጥሬው የዕብራይስጥን ልዕለ ማወዳደሪያ መፍጠሪያ መንገድ ነው፣ ኢሳ. 6፡3፣ ወይም አጽንዖትን መግለጫ ቅኔአዊ መንገድ፣ መዝ. 103፡10፣21፣22፤ 118፡2፣3፣4፤ 135፡1፤ 136፡1፣2፣3፤ኤር. 7፡4፤ 22፡29)። እሱም የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው፣ "ምድር ሁሉ" ለእሱ ይዘምርና ይባርከው ዘንድ። እሱም የእስራኤል ተግባር ነው፣ የያህዌ ባሕርይና ድርጊቶች ለዓለም ይታወቁ ዘንድ ማድረግ። ፍጥረት ሁሉ እሱን ያመሰግነዋል (መዝ. 96፡11-12፤ 103፡19-22፤ 145፡10)።

▣ **"አዲስ ዝማሬ"** ይህ ሐረግ ዘወትር በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም ላይ ውሏል (መዝ. 33፡3፤ 40፡3፤ 98፡1፤ 144፡9፤ ኢሳ. 42፡10፤ ራዕ. 5፡9፤ 14፡3)። እግዚአብሔር ዘወትር አዲስ የማዳን ነገር ያደርጋል፣ ለሰብዓዊ ፍጥረቱ። ይህም አሕዛብን ሁሉ ለማዳን መምጣቱን ለመጥቀስ ይመስላል (መዝ. 96፡13)።

"አዲስ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 294  l፣ መዝ. 33፡3፤ 40፡3፤ 90፡1፤ 98፡1፤ 144፡9፤ 149፡1) ኢሳይያስ ላይ ተዘውትሮ ጥቅም ላይ ውሏል፣ የያህዌን አዲስ የፍጥረት ተግባር ለመግለጽ። "አዲስ" በርግጥ ያህዌ ዋነኛው ፍጥረት እንዲሆን የሚፈልገው ነው። የውድቀት ውጤትና ተጽዕኖ ተቀልብሷል ጠፍቷልም! መጽሐፍ ቅዱስ የጀመረው በዔድን ነው (ዘፍጥረት 1-4) የሚያበቃውም በአዲሲቷ ዔድን ነው (ራዕይ 21-22)።

ኢሳይያስ ይሄንን ቃል ብዙ ነገሮችን ለመግለጽ ተጠቅሞበታል።

1. አዲስ ነገሮች –ኢሳ. 42፡9፤ 48፡6
2. አዲስ ዝማሬ – ኢሳ. 42፡10 (ራዕ. 5፡9፤ 14፡3)
3. አዲስ የሆነ ነገር – ኢሳ. 43፡19 (ራዕ. 3፡12)
4. አዲስ ስሞች – ኢሳ. 62፡2 (ራዕ. 2፡17፤ 3፡12)
5. አዲስ ሰማይ እና አዲስ መሬት – ኢሳ. 65፡17፤ 66፡22 (2 ጴጥ. 3፡13፤ ራዕ. 21፡5)

▣ **"ምድር ሁሉ"** ይህ ሁለንተናዊ ጭብጥ አሁንም አሁንም ይደጋገማል፣ በዚህ መዝሙር ላይ በድጋሚ (መዝ. 96፡3፣7፣ 9፣10፣13)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር። እባክዎን፣ እባክዎን ጊዜ ወስደው ልዩ ርዕሴን ይመልከቱ፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ። እሱ የእኔ ሥነ-መለኮት የተቀናጀ ማዕከል ነው።

**96፡2 "ስሙን ባርኩ"** ይሄም ደግሞ ተተኳሪ ነው (ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ ፔይል)። የቃሉ ሥር ፍች "መንበርከክ" ማለት ነው፣ በአምልኮ። ስለዚህ፣ ይህ የመቅደስ የአምልኮ ሥርዓት ወይም ኑዛዜ ነው (መዝ. 26፡12፤ 100፡4፤ 134፡1-2፤ 135፡19-20፤ ነህ. 9፡5)።

▣ **"መልካሙን ምስራች አውጁ"** ይህ ሌላው ፒኤል ተተኳሪ ነው (ቢዲቢ 142፣ ኬቢ 163)። መልካሙ የምስራች የያህዌን ባሕርይ ወይም የእርሱን የማዳን/የመዋጀት ሥራ የሚጠቅስ ይሆናል (ኢሳ. 40፡9፤ 41፡27፤ 52፡7፤ 60፡6፤ ናሆ. 1፡15)። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ እሱ የሚያመለክተው የያህዌ ምድርን ሁሉ ማዳኑን ነው ("አውሩ" የመዝ. 96፡3ሀ ትይዩ ነው፣ እንዲሁም ደግሞ ፒኤል ተተኳሪ፣ ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765)።

▣ **"ዕለት ዕለትም"** ኤቢ ስለዚህ አስደናቂ ነጥብ ያስቀምጣል

1. በታሳቢነት፣ ים – ባሕር እና יום – ቀን በፍንቄአውያን በተመሳሳይ መልኩ ፊደል ተደርጎላቸዋል (ገጽ 357)
2. ከባሕር ወደ ባሕር (መዝ. 72፡8፤ ዘካ. 9፡10) ከመዝሙሩ ሁለንተናዊ ጠባይ ጋር በተሻለ ይገጥማል (ገጽ 357) ደግሞም "ባሕሮች" መዝ. 96፡11 ላይ ተጠቅሰዋል።

▣ **"ደኅንነት"** በብኪ ይህ (ቢዲቢ 447) የሚጠቅሰው አካላዊ ትድግናን (መታደግ) ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት [ብኪ])፣ ነገር ግን አኪ ላይ ፍችው ወደ መንፈሳዊ ትድግና ይለወጣል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የግሪክ ግሥ ጊዜያት፣ ለደኅንነት ጥቅም ላይ የዋሉ)። ይህ የፍጻሜ ዘመን መዝሙር ሁለቱን ኪዳናት ይጠቅሳል፣ ሁለቱንም ገጽታዎች ያያይዛል።

**96፡3 "ክብር"** ይህ ቃል መዝ. 96፡3፣7፣8 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል። እሱም በብኪ ሰፋ ያለ አጠቃቀም አለው። እሱም የመጣው ከንግድ አጠቃቀም ነው፣ "ከባድ መሆን" እንደ ከበረ ድንጋይ (ብረት)። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው

1. ለያህዌ ስም – መዝ. 29:2፤ 66:2፤ 96:8
2. ለያህዌ አካል – ዘጸ. 24:16-17፤ 33:18፣22፤ 40:34-35፤ ዘኍ. 14:22
3. ለያህዌ ድርጊቶች – ዘጸ. 16:7፣12

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ክብር (ካቦድ፣ ብኪ)።

▣ **"አስደናቂ ድርጊቶቹ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አስደናቂ ነገሮች (ተአምራት)።

**96፡4 "ታላቅ ምስጋናውም ብዙ ነውና... የተፈራ ነውና።"** ይህ ከመዝ. 48፡1 ጋር ተመሳሳይ ነው። እነዚህ ሁለቱ አንድ ላይ የሚሄዱ አይመስሉም፣ ሆኖም ግን ሁለቱም ስለ እግዚአብሔር ተገቢ አዝማሚያ ያንጸባርቃሉ። "ፍርሃት" (ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ ኒፋል አንቀጽ) ማለት አግርሞት ወይም አክብሮት ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፍርሃት [ብኪ])።

▣ **"በአማልክትም ሁሉ ላይ"** መዝሙር 96፡4 እና 5 የሚናገሩት ስለ "ሕዝብ ኤሎሂም (አለቆች)" ነው። እዚህጋ የዕብራይስጥ የቃላት መቀያየር (ጨዋታ) አለ፣ በ "አማልክት" — *ኤሎሂም* (ቢዲቢ 43፣ 96:4) እና "ጣዖታት" – *ኤሊሊም* ("ደካማ፣" "ምናምን፣" መካከል ቢዲቢ 47፣ መዝ. 96:5፤ ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 411)።

አለቆች (ኤሎሂም) የአሕዛብ የሚታሰቡት እንደ ወደቁ መላእክት ነው፣ በቀድሞ የቤተ-ክርስቲያን አባቶች፣ ግን በ'ርግጥ፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የሚያመለክተው የየአምልኮተ-ባዕድ ጣዖታትን ነው፣ መዝ. 89፡5፣7 የሚያመለክተው ደግሞ የመላእክትን ጉባኤ ነው። *ኤሎሂም* የሚለው ቃል ሊያመለክት የሚችለው (1) ያህዌን፤ (2) ሰብዓዊ ፈራጆችን ወይም መሪዎችን፤ ወይም (3) መላእክትን (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች)።

**96፡5 "እግዚአብሔር ግን ሰማያትን ሠራ"** የያህዌ ልዕልና ዓለምን በመፍጠሩ ተረጋግጧል (መዝ. 96:10፣11-12)። እሱ እና እሱ ብቻ ነው ፈጣሪ!

**96፡6** ሰዋኛ ስሞቹን ተገንዘብ (መዝ. 23፡6) የያህዌን አካላዊ መገኘት ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን።

1. ድንቅ – ቢዲቢ 217 I፣ cf. 1 ዜና. 16:27፤ 29:11፤ መዝ. 104:1፤ 111:3፤ 145:5፤ 148:13፤ ኢዮብ 37:22፤ 40:10፤ ዕን. 3:3
2. ግርማ – ቢዲቢ 214፣ cf. 1 ዜና. 16:27፤መዝ. 90:16፤ 104:1፤ 111:3፤ 145:5፤ኢዮብ 40:11፤ ኢሳ. 2:10፣19፣21
3. ብርታት – ቢዲቢ 738፣ 1 ዜና. 16:27፤ ኢዮብ 12:16፤ መዝ. 62:11፤ 63:2፤ 68:34፤ 93:1
4. ውበት – ቢዲቢ 802፣ 1 ዜና. 29:11፤ መዝ. 71:8፤ 89:13፤ ኢሳ. 63:12፣14፣15

የዩቢኤስን ማስታወሻ መጽሐፍ ሐሳብ እወደዋለሁ፣ ይኸውም ቁ. 1 እና ቁ. 2 ንጉሣዊ ቃላት ሲሆኑ (መዝ. 21፡5፤ 45፡3)፣ ቁ. 3 እና 4 ደግሞ ከኪዳኑ ታቦት ጋር ይዛመዳሉ፣ መዝ. 78፡61 ላይ (ገጽ 834)። ስንኝ (መስመር) አንድ "በፊቱ" በሚል እንደሚያበቃ ተገንዘብ (ያህዌ እንደ ንጉሥ) እንዲሁም ስንኝ ሁለት "በመቅደሱ"፣ እሱም ታቦቱን የያዘ!

ለተሻለ ማብራሪያ

1. ሰውኛነት ወይም ሰዋዊነት (አንትሮፖሞርፊም) በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ጂ. ቢ. ካሪድ፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ እና ምናባዊነት*፣ ገጽ 172-182
2. በመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም ላይ የዋለ አፈ-ታሪክ፣ ገጽ 219-242
3. የመጨረሻው ዘመን በመጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 243-271

ይህ መጽሐፍ እጅግ ረድቶኛል፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጽሑፋዊ ምናባዊነት ላይ!

▣ **"በመቅደሱ"** ይህ የሚያመለክተው ሰማያዊውን ቤተ-መቅደስ ነው (ዘጸ. 25፡8-9) ወይም ምድራዊውን መቅደስ ሊሆን ይችላል። ምድራዊው የሰማያዊው ትክክለኛ ግልባጭ ነው (ዕብ. 8፡5፤ 9፡23)። የ 1 ዜና መዋዕል 16 የምስጋና መዝሙር፣ ግልጽ በሆነ መልኩ ምድራዊ ነው (ዕብራውያን 9-10)።

***መዝሙር ፡ 96፡7-10***

**[7]የአሕዛብ ወገኖች፥ ለእግዚአብሔር አምጡ፥**
**ክብርና ምስጋናን ለእግዚአብሔር አምጡ**
**[8]ለስሙ የሚገባ ክብርን ለእግዚአብሔር አምጡ**
**ቍርባን ያዙ ወደ አደባባዮችም ግቡ።**
**[9]በቅድስናው ስፍራ ለእግዚአብሔር ስገዱ**
**ምድር ሁሉ በፊቱ ትነዋወጥ።**
**[10]በአሕዛብ መካከል። እግዚአብሔር ነገሠ በሉ።**
**እንዳይናወጥም ዓለሙን እርሱ አጸናው፥**
**አሕዛብንም በቅንነት ይፈርዳል።**

**96፡7 "አምጡ"** ይህ ሦስትዮሽ ድግግሞሽ (ሦስት ቃል ተተኳሪ፣ ቢዲቢ 396፣ ኬቢ 393) መዝ. 29:1-2ን ያጸባርቃል፣ መላክት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑ። እዚህ የምድር ሕዝቦች ሁሉ ናቸው። የአህዳዊነት አንድምታ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አህዳዊነት) ሁለንተናዊ ነው እንጂ ብሔራዊ አይደለም። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

**96፡8 "ለስሙ የሚገባ ክብር"** ስም ግለሰብን ይወክላል (ኢሳ. 42፡8፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጥላ ለጥበቃና ክብካቤ እንደ ዘይቤ)። እርሱ ምስጋናና ክብር ይገባዋል (ለ "ክብር" ፍች፣ በዚህ ጽሑፍ ላይ ሚል. 1፡6)። ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (1 ዜና. 16:29፤ መዝ. 29:2፤ 66:2፤ 79:9)።

▣ የዚህ ቁጥር ሁለተኛው ስንኝ ሁለት ቃል ተተኳሪዎች አሉት።

1. ቁርባን አምጡ – ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724
2. ወደ አደባባዮቹም ግቡ – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112

እንደ መጀመሪያው አንጓ (መዝ. 96፡1-6)፣ ይህም የመቅደስ አምልኮን ያመለክታል።

**96፡9 "አምልኩት... ትነዋወጥ"** እነዚህ ሁለት ተተኳሪዎች ናቸው፣ ከመቅደስ ድርጊቶች ጋር የሚዛመዱ።

1. አምልኮ ("መስገድ") – ቢዲቢ 1005፣ ኬቢ 295፣ *ሂዝፓል* ወይም *ሂሽታፌል*)፣ መዝ. 29:2
2. መንቀጥቀጥ – ቢዲቢ 296፣ ኬቢ 297፣ *ቃል፣* ቃሉ የሚጠቅሰው
   ሀ. በአክብሮት መንቀሳቀስ
   ለ. የሽብሸባ አምልኮ (መዝ. 96:8፤ አአመቅ እና መሳ. 21:21)
   ሐ. በመሽከርከር፣ በሰይፍ እንደሚሆን ግጥሚያ
   መ. መንቀጥቀጥ
      (1) ምድር፣ መዝ. 97:4፤ 104:32፤ 114:7
      (2) ሰብዓዊ አምላኪዎች (ምዕመናን) መዝ. 96፡9 (ማለትም፣ ፍርሃትና አክብሮት)

▣ **"በቅድስናው ስፍራ"** ይህ ሐረግ (ቢዲቢ 214 አወቃቀር ቢዲቢ 871) በዕብራይስጥ ርግጠኝነት የለውም። ሊሆን የሚችለው (1) ለአምልኮ በተገቢ መልኩ መልበስ (1 ዜና. 16:29፤ 2 ዜና. 20:21፤ መዝ. 29:2፤ 110:3) ወይም (2) ለጌታ መምጣት መጥቀሻ (መዝ. 96፡13፣ አእቅ)።

ለመጀመሪያው አማራጭ ታሳቢ ማብራሪያ ይመስላል (ማለትም፣ ለአምልኮ ሥርዓት ተገቢ አለባበስ)። *ሔሊልም* የሚለው ቃል (ቢዲቢ 43) የማይወዘተር የዕብራይስጥ ቃል ነው። ኤቢ የሚለው እሱ ከዑጋሪቲካዊ ቃል "ቁጣ" ጋር ይዛመዳል (ገጽ 356፣ 358)። እንደዛ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ተቃርኗዊ ቅንብር (አደረጃጀት) አለ፣ የያህዌ አምላኪዎች እንዴት እንደሚለብሱ (መዝ. 96፡9) እና የአምልኮተ-ባዕድ ጣዖታት የሚለብሱበት አስፈሪ መንገድ (መዝ. 96፡5) እና የሚመለኩበት።

**96፡10 "እግዚአብሔር ነገሠ"** ይህ የተለመደ ማረጋገጫ ነው፣ በመዝሙራት ላይ (መዝ. 93:1፤ 97:1፤ 99:1)። እሱም የያህዌን ንጉሥነት ይጠቅሳል፣ በፍጥረት ሁሉ ላይ (መዝ. 95፡3-5)። እሱ አሁን ይነግሣል (ኢሳ. 52፡7) ነገር ግን ንግሥናው ተቀናቃኝ አለው። አንድ ቀን የእርሱ ንግሥና በገሀድ ይገለጣል (መዝ. 96:13፤ ዘካ. 14:9፤ ማቴ. 6:10፤ 1 ቆሮ. 15:25-28)።

**96፡10 "እንዳይናወጥም ዓለሙን እርሱ አጸናው፥"** በዚህ አንጓ ላይ ይህ ሐረግ የመነሻ ፍጥረትን አያመለክትም (ዘፍጥረት 1-2) ነገር ግን አዲሱን ፍጥረት እንጂ (ራዕይ 21-22፤ 2 ጴጥ. 3:4-7፤10-13)። ይህ ዓለም በኃጢአትና በዓመጻ ተጎድቷል። እሱም ለረጅም ጊዜ የሚቆይ ነው፣ ነገር ግን በቋሚነት አይደለም። ይህ የተናወጠ ዩኒቨርስ ነው። እግዚአብሔር ካልሠራ ይህ ዓለም የሚጠርፍ አይደለም።

▣ **"አሕዛብንም በቅንነት ይፈርዳል"** አንድ አምላክ ብቻ ነው ያለው። እሱም ጻድቅ፣ ሥነ-ምግባራዊ፣ ኪዳንን የሚያበጅ አምላክ ነው! ሥጋ ሁሉ ለእርሱ ምላሽ ይሰጣል (ዘፍ. 18:25፤ መዝ. 9:8፤ 58:11፤ 67:4፤ 94:2፤ 98:9፤ ማቴ. 25:31-46፤ ራዕ. 20:11-15)!

### መዝሙር ፡ 96፡11-13

**11 ሰማያት ደስ ይበላቸው፥ ምድርም ሐሤትን ታድርግ**
**ባሕርና ሞላዋ ይናወጡ**
**12 በረሃ በእርስዋም ያሉ ሁሉ ሐሤትን ያድርጉ**
**የዱር ዛፎች ሁሉ በዚያን ጊዜ በእግዚአብሔር ፊት ደስ ይላቸዋል**
**13 ይመጣልና**
**በምድር ላይ ሊፈርድ ይመጣልና**
**እርሱም ዓለምን በጽድቅ**
**አሕዛብንም በቅንነት ይፈርዳል።**

**96፡11-12** ፍጥረት ሁሉ ይደሰታል (ሰውኛ ዘይቤ) በፈጣሪ መምጣት (መዝ. 103:19-22፤ 145:10፤ ኢሳ. 49:13፤ ሮሜ. 8:19-22)።

ተጽዕኗዊዎቹን ሁሉ ተገንዘብ።

1. ሰማያት ደስ ይበላቸው – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፤ ለ "ሰማያት" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማይ
2. ምድርም ሐሤትን ታድርግ – ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189፣ *ቃል* ተጽዕኗዊ፤ የ "ሰማይ" እና "ምድር" አጠቃቀም ፈሊጣዊ መንገድ ነው፣ ፍጥረት ሁሉ እግዚአብሔርን እንዲያመሰግን ጥሪ ለማድረግ (ዘፍ. 1:1)
3. ባሕርም ትናወጥ ቢዲቢ 947፣ ኬቢ 1266፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፤ ባሕር ሊወክል የሚችለው (1) የመነሻውን የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አማልክት ሁከት (መዝ. 89:9-10፤ 93:3-4) ወይም (2) ባለ ሦስትዮሽ ይዘት ፍጥረትን እንደሆነ አስታውስ (ማለትም፣ "ሰማያት፣" "ምድር፣" "ባሕር፣" አሞጽ 9:6፤ ሐጌ. 2:6፤ ኒዶቲ፣ ቅጽ. 2፣ ገጽ 463-465 ተመልከት)
4. በረሃም ሐሤትን ታድርግ– ቢዲቢ 759፣ ኬቢ 831፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

5. የዱር ዛፎች. . . በደስታ ይዘምሩ – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ ፒል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

**96፡13 “ይመጣልና”** በአንድ መልኩ ያህዌ ዘወትር ከፍጥረቱ ጋር ነው። እሱም ለፍጥረቱ የእርሱን መገኘት በገሀድ ሲገልጽ ነው። ፍጥረት በእርሱ መገኘት ሐሤት ያደርጋል፣ ይደሰታልም። እሱም ይመጣል

1. ለበረከት
2. ለፍርድ

ይህ ሐረግ (ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል አንቀጽ*) ለአጽንዖት ተደግሟል፣ እንደ ጸሎት እና እንደ ማረጋገጫ።

ልዩ ርዕስ፡ የዳግም ምጽአቱ ቃላት

▣ **“በጽድቅ... በታማኝነት”** እነዚህ በትይዩነት ግንኙነት ናቸው። እግዚአብሔር እውነትና የታመነ ነው። እሱም ሁሉንም ነገር ያስተካክላል! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ እና ልዩ ርዕስ፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ። ይህ ጽንሰ-ሐሳብ ደግሞ መዝ. 96፡10ሐ ላይ ተጠቅሷል (ማለትም፣ ጽድቅና፣ መዝ. 75፡2፤ 98፡9)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ለአዲስ ኪዳን ብሎም ለብሉይ ኪዳን እጅግ ጠቃሚ የሆነው እንዴት ነው?
2. የዚህን መዝሙር ዩኒቨርሳል (ሁለንተናዊ) ይዘት ዘርዝር። የእነርሱስ አንድምታ ምንድነው?
3. በያህዌ መምጣት ፍጥረት የሚደሰተው ለምንድነው?
4. የፍርድ ቀን ለደስታ እንዴት ይሆናል?

# መዝሙር 97
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጌታ ኃይልና ገዥነት<br>ኤምቲመግቢያ የለውም | የምስጋና ዝማሬ ለሉዓላዊው አምላክ | ውዳሴ የእግዚአብሔርን ንግሥና ለማክበር | እግዚአብሔር ሉዓላዊው ገዥ | የያህዌ ድል ነሺነት |
| 97:1-6 | 97:1 | 97:1-5 | 97:1-6 | 97:1-2 |
| | 97:2-6 | | | |
| | | | | 97:3-4 |
| | | | | 97:5-6 |
| | | 97:6-9 | | |
| 97:7-9 | 97:7-9 | | 97:7-9 | 97:7 |
| | | | | 97:8 |
| | | | | 97:9 |
| 97:10-12 | 97:10-12 | 97:10-12 | 97:10-12 | 97:10 |
| | | | | 97:11-12 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ

2. ሁለተኛው አንቀጽ

3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር፣ እንደ መዝሙር 96 ዓለም-አቀፍ አጽንዖት አለው (የፍጻሜ ዘመናዊ)።
1. ምድር፣ መዝ. 97:1 (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር)
2. ዓለም፣ መዝ. 97፡4
3. ጌታ (*አዶን*) የምድር ሁሉ፣ መዝ. 97:5ለ (ኢያ. 3:13፤ ሚክ. 4:13)
4. ሕዝቦች ሁሉ፣ መዝ. 97:6ለ
5. አንተ ጌታ ልዑሉ ነህ በምድር ሁሉ ላይ፣ መዝ. 97፡9ሀ
6. ከአማልክት ሁሉ በላይ ከፍ ያልክ ነህ (ኤሎሂም)፣ መዝ. 97፡9ለ

ለ. ምናባዊው (ምስያ) ሊመጣ የሚችለው
1. የሲና ተራራ፣ ዘጸአት 19 (ማለትም፣ በረከቶች፣ ዘጸ. 19፡9፤ ዘዳ. 4፡11)
2. መዝሙር 18፡7-15 (ማለትም፣ ፍርድ)

የያህዌ ለባርኮት ወይም ለፍርድ መገኘት በሥጋዊ ፍጥረት ላይ መናወጥን ያመጣል (መዝሙር 97፡4-5)።

ሐ. የመጨረሻው አንጓ የመታዘዝ ገጽታን ያጎላል፣ ለኪዳን እምነት። ዘወትር እንደምለው የመሰለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት
1. ግለሰቡን በደንና መቀበል
2. ስለ እዛ ግለሰብ መታመን ያለ እውነት

3. ያንን ግለሰብ የመሰለ ሕይወት መኖር

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 97፡1-6**

**[1]እግዚአብሔር ነገሠ ምድር ሐሤትን ታድርግ፥**
**ብዙ ደሴቶችም ደስ ይበላቸው።**
**[2]ደመና ጭጋግም በዙሪያው ናቸው**
**ጽድቅና ፍርድ የዙፋኑ መሠረት ናቸው።**
**[3]እሳት በፊቱ ይሄዳል፥**
**ጠላቶቹንም በዙሪያው ያቃጥላል።**
**[4]መብረቆቹ ለዓለም አበሩ**
**ምድር አየችና ተናወጠች።**
**[5]ተራሮችም ከእግዚአብሔር ፊት፥**
**ከምድር ሁሉ ጌታ ፊት እንደ ሰም ቀለጡ።**
**[6]ሰማያት የእርሱን ጽድቅ አወሩ፥**
**አሕዛብም ሁሉ ክብሩን አዩ።**

**97፡1-6** *ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘቱን ተመልከት ሀ እና ለ።*

**97፡1 "እግዚአብሔር ነገሠ"** *ግሡ ቃል* የተጠናቀቀ (ቢዲቢ 573 II፣ ኬቢ 590፣ 1 ዜና. 16፡31፤መዝ. 93፡1፤ 96፡10፤ 97፡1፤ 99፡1)፣ ይኸውም የተጠናቀቀ ድርጊትን የሚገልጽ። በአንድ መልኩ፣ ያህዌ ዘወትር ይገዛል፣ እየገዛ ነው፣ እናም ለዘላለም የገዛል (ማለትም፣ እሱ አምላክ ነው፣ ዘጸ. 15፡18፤ መዝ. 10፡16፤ 29፡10፤ 1 ቆሮ. 15፡24-28)፣ ነገር ግን የዚህ ማስረጃ ዘወትር እንደ ጠፋ ነው፣ በዚህ በወደቀ ዓለም። እምነት ይመለከታል ያጸናልም፣ ነገር ግን አንድ ቀን ሁሉም ይገነዘባሉ ያጸናሉም።

ያልተጠናቀቀው መዝ. 146፡10 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እናም የወደፊቱ ንግሥና ኢሳ. 24፡23፤ ሕዝ. 20፡23 እና ሚክያስ 4፡7 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል። አሁን እናውቃለን፣ ከአኪ መገለጥ፣ የመሲሑ አገዛዝ (ዘካ. 9፡9) በአብ አገዛዝ ውስጥ መካተቱን (ኤር. 23፡5፤ ፊሊ. 2፡6-11፤ 1 ቆሮ. 15፡24-28)። ነገሮች ክፉ ሊመስሉ ይችላሉ ነገር ግን አማኞች ያውቃሉ፣ "አምላካችን ነግሧል" (ኢሳ. 52፡7)

▣ ከያህዌ አገዛዝ አኳያ፣

1. ምድር ሐሤት ታድርግ – ቢዲቢ 162፣ ኬቢ 189፣ *ቃል* ተጽዕኖዊ፤ ይህ የሚያመለክተው
   ሀ. በሁሉም ሕዝቦች ያሉትን ታማኝ ተከታዮች
   ለ. የአሕዛብን መለወጥ፣ በያህዌ ወደ ማመን
2. ብዙ ደሴቶችም ደስ ይበላቸው – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፤ "ደሴቶች" ("የባሕር ዳርቻች" ቢዲቢ 15) ሁለንተናዊ አጽንዖትን ያመለክታል (መዝሙር 96)፣ ዘወትር የሚታወቀውን ዓለም የሚጠቅስ (ማለትም፣ እነዚያን ወደቦች፣ በቅርበትና በርቀት ያሉትን፣ በፍንቄአውያን ግብይት የሚጎበኙትን፣ ማለትም፣ መዝ. 72፡8-10)። "ምድር" ስንኝ 1 ላይ ያለው ከ "ብዙ ደሴቶች" ከሚለው ጋር ትይዩ ነው፣ ስንኝ 2 ላይ ካለው።

**97፡2** የመዝ. 97፡2ሀ ምናባዊ (ምስያ) ከሁለት ምንጮች ሊመጣ ይችላል። ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ለ ተመልከት። በዚህ አንጓ ላይ የመገለጥን አምላክ የሚያንጸባርቅ ይመስላል (ማለትም፣ ቲዎፋኒ (የመለኮት መገለጥ))፣ ፍርድን ሳይሆን። የእርሱ ጠላቶች ተሸንፈዋል፣ ነገር ግን የምድር ሁሉ ታማኞች ደስ ይላቸዋል፣ "በብርሃኑ" እና በመገኘቱ!

▣ **"ደመና"** "የደመናት" አጠቃቀም በሁለቱም በብኪ እና አኪ እጅግ አስደናቂ ነው። ማስታወሻዎችን ከዘዳ. 4፡11 እና ራዕ. 1፡7 አካትቻለሁ።

**ዘዳ. 4፡11 "ጨለማ፣ ደመና እና ድቅድቅ ጨለማ"** የያህዌን አካላዊ መገኘት በሁለት መንገዶች መረዳት ይቻላል፡
1. እሳተ-ገሞራዊ እንቅስቃሴዎች – ዘጸ. 19፡18፤ መዝ. 68፡7-8፤ 77፡18፤ 97፡2-5፤ መሳ. 5፡4-5፤ 2 ሳሙ. 22፡8፤ ኢሳ. 29፡6፤ኤር. 10፡10
2. ማዕበል – ዘጸ. 19፡16፣19፤ መዝ. 68፡8፤ 77፡18፤ መሳ. 5፡4፤ ኢሳ. 29፡6፤ ናሆም 1፡3

ስለዚህ፣ ድቅድቁ ጨለማ (ዝኪ. 5፡22፤ II ሳሙ. 22፡10፤ 1 ነገ. 8፡12፤ II ዜና. 6፡1) ሊሆን የሚችለው፡
1. ብናኝ ደመና
2. የዝናብ ደመና

ይህ ሽፋን ለእስራኤል ከለላ ነው (ዘጸ. 19፡18)። እነርሱ የሚያስቡት፣ ሰዎች እግዚአብሔርን ከተመለከቱ ይሞታሉ ብለው ነው (ዘፍ. 16፡13፤ 32፡30፤ ዘጸ. 3፡6፤ 20፡19፤ 33፡20፤ መሳ. 6፡22-23፤ 13፡22)።

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ከደመና ጋር ይመጣል።

**ራዕ. 1፡7 "እነሆ፣ ከደመና ጋር ይመጣል"** ይህ ቁጥር በመልአክ የተደረገ አጽንዖታዊ ገለጻ ሊሆን ይችላል፣ ራዕ. 1፡1። እሱም ግልጽ የሆነ ጠቃሽ ነው፣ ለክርስቶስ ዳግም ምጽአት።

▣ **"ጽድቅና ፍርድ የዙፋኑ መሠረት ናቸው።"** "ዙፋን" ፈሊጥ ነው ለገዥነት/ንግሥና።
የያህዌ አገዛዝ ሥነ-ምግባራዊ ገጽታ አለው፣ ፍጥረቱ እንዳለው ሁሉ (መዝ. 97፡10-12)።

ይኸው ተመሳሳይ ሐረግ መዝ. 89፡14 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል። መጠንቀቅ ይኖርብናል፣ ጽድቅን ከቅድስና ላለመለየት (ማቴ. 28፡18-20)።

**97፡3 "እሳት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እሳት።

▣ **"ጠላቶቹንም በዙሪያው ያቃጥላል።"** ኤቢ. የሚለው በዕብራይስጥ የኤምቲ የመጨረሻው ሐረግ "እና ነበልባል በጀርባው በኩል" በሚል ሊነበብ ይችላል (ገጽ 361)። ይኸው ሐሳብም በተሻለ የሚብራራው መዝ. 50፡3 እና ኢዩኤል 2፡3 ላይ ነው። ይኸም የመዝ. 97፡4 ትይዩ በተሻለ ይገጥማል።

**97፡4 "ምድር"** ልክ እንደ ሌሎቹ በርካታ ስሞች፣ በዚህ መዝሙር ላይ፣ ይህ ሰውኛ ዘይቤ ነው፣ የተለመደ የዕብራይስጥ ቅኔ ብልሃት።

**97፡6** ይህ ቁጥር ከሥነ-መለኮት አኳያ እና ከሥርወ-ቃል አንጻር ከመዝ. 19፡1-6 ጋር ይዛመዳል። የያህዌ ራዕይ ሁለንተናዊ ገጽታ በፍጥረት/ተፈጥሮ ላይ ተገልጧል (ማለትም፣ ተፈጥሯዊ መገለጥ፣ ሮሜ. 1:19-20፤ 2:14-15)። ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 19፡1-6 ላይ።

**መዝሙር ፡ 97፡7-9**

**7ለተቀረጸ ምስል የሚሰግዱ ሁሉ፥**
**በጣዖቶቻቸውም የሚመኩ ይፈሩ**
**መላእክቱ ሁሉ፥ ስገዱለት።**
**8አቤቱ፥ ስለ ፍርድህ**
**ጽዮን ሰምታ ደስ አላት፥**
**የይሁዳም ሴት ልጆች ደስ አላቸው**
**9አንተ፥ እግዚአብሔር፥ በምድር ላይ ሁሉ ልዑል ነህና፥**
**በአማልክትም ሁሉ ላይ እጅግ ከፍ ከፍ ብለሃልና።**

**97፡7-9** ሦስት አካላት በዚህ አንጓ ላይ ተመልክተዋል።

1. አመንዝራዎች (ጣዖት አምላኪዎች)፣ መዝ. 97፡7
   ሀ. ይፈሩ (ቢ.ዲ.ቢ. 101፣ ኬቢ. 116፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ)
   ለ. የሚመኩ ("ክብር፣" ቢ.ዲ.ቢ. 237፣ ኬቢ. 248፣ *ሂዝፓል*)
   ሐ. የእነርሱ ሐሰተኛ አማልክት እንኳ ለያህዌ መስገድ ይኖርባቸዋል (ቢ.ዲ.ቢ. 1005፣ ኬቢ. 295፣ *ሂሽታፌል ተተኳሪ*፣ ዕብ. 1:6 ላይ ተጠቅሷል፣ ከLXX፣ ዘዳ. 32:43 LXX ላይ)
2. የይሁዳም (ወይም እስራኤላውያን)፣ መዝ. 97:8
   ሀ. ጽዮን ደስ አላት (ቢ.ዲ.ቢ. 970፣ ኬቢ. 1333፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ ከ*ዋው ጋር*፣ መዝ. 48:11)
   ለ. የይሁዳም ሴት ልጆች (ቢ.ዲ.ቢ. 162፣ ]ኬቢ. 189፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ ከ*ዋው ጋር*) በያህዌ ፍርድ ምክንያት
   ሐ. በርግጠኝነት የሚሆነው ቁ. ሀ ከላይ ኢየሩሳሌምን ሲወክል እንዲሁም ቁ. ለ ያካባቢውን ያልተመሸጉ (ቅጥር የሌላቸው) መንደሮች ነው
3. የእስራኤል አምላክ፣ መዝ. 97፡9
   ሀ. ያህዌ (ቢ.ዲ.ቢ. 217)
   ለ. ልዑሉ (ኤሊዮን፣ ቢ.ዲ.ቢ. 75፣ መዝ. 47:2)
   ሐ. ከፍ ያለ (ቢ.ዲ.ቢ. 748፣ ኬቢ. 828፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ) ከአማልክት ሁሉ በላይ (ኤሎሂም፣ መዝ. 95፡3 ላይ ማስታወሻ ተመልከት)

**97፡7 "የተቀረጹ ምስሎች… ጣዖታት"** እነዚህ በትይዩ ቅኔአዊ ዝምድና ናቸው።

1. የተቀረጹ ምስሎች – ቢ.ዲ.ቢ. 820፤ መሠረታዊ ፍችው ወደ ቅርጽነት የተለወጠ ነው (ዘጸ. 20:4፤ ዘዳ. 4:16፣23፣25፤ 5:8፤ 27:15፤ መሳ. 18:31፤ ኢሳ. 40:19፣20፤ 42:17፤ 44:9፣10፣17፤ 45:20)። መዝሙር ላይ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ነገር ግን ተዛማጅ ሥር መዝ. 78:58 ላይ አለ።
2. ጣዖታት – ቢ.ዲ.ቢ. 47፤ መሠረታዊ ፍችው ደካማ፣ ብቃት የሌለው፣ ጥቅመ-ቢስ ነው (1ዜና. 16:26፤ ኢዮብ 13:4፤ መዝ. 96:5፤ኢሳ. 2:8፣18፣20፤ ኤር. 14:14)። መዝሙር ላይ ሁለቱ ብቻ ነው የሚገኘው።

**መዝሙር ፡ 97፡10-12**

**10እግዚአብሔርን የምትወዱ፥ ክፋትን ጥሉ**
**እግዚአብሔር የቅዱሳኑን ነፍሶች ይጠብቃል፥**
**ከኃጥአንም እጅ ያድናቸዋል።**
**11ብርሃን ለጻድቃን፥**
**ደስታም ለልበ ቅኖች ወጣ።**
**12ጻድቃን፥ በእግዚአብሔር ደስ ይበላችሁ፥**
**ለቅድስናውም መታሰቢያ አመስግኑ።**

**97፡10-12** ይህ አንጓ ተገቢውን መንገድ ይገልጻል፣ እግዚአብሔርን ከፍ ለማድረግ። እሱም አንዱ ነው

1. ነፍሳትን የሚጠብቅ (*ሂፊሽ፣* ቢ.ዲ.ቢ. 659፣ ዘፍ. 35:18 ላይ ማስታወሻ ተመልከት፣ በድረ-ገጽ) የቅዱሳኑን (ቢ.ዲ.ቢ. 339፣ መዝ. 31:23 ላይ ማስታወሻ ተመልከት)
2. ከኃጥአንም እጅ ያድናቸዋል
3. ብርሃን ለጻድቃን ይወጣል (መዝ. 97፡4ሀ)
4. ደስታም ለልበ-ቅኖች ይወጣል

እንግዲያውስ ቅዱሳኑ እንዴት ምላሽ ይሰጣሉ?

1. ክፋትን በመጥላት – ቢ.ዲ.ቢ. 971፣ ኬቢ. 1338፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. እግዚአብሔርን በመውደድ – ቢ.ዲ.ቢ. 12፣ ኬቢ. 17፣ *ቃል አንቀጽ*
3. በጌታ ደስ በመሰኘት – ቢ.ዲ.ቢ. 970፣ ኬቢ. 1330፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 32:11
4. ለቅዱስ ስሙ ምስጋናበማቅረብ – ቢ.ዲ.ቢ. 392፣ ኬቢ. 389፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 30:4

**97:11 "ብርሃን ወጣ"** ኤምቲ "ወጣ" የሚል አለው (ﬠרז ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 281፣ ኬቢ. 282) ነገር ግን LXX፣ ፔሺታ፣ እና ቫልጌት "ንጋት" የሚል አላቸው (זרח ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 280)፣ ይኸውም ከምናባዊው ምስያ ጋር በተሻለ የሚገጥም (አየተመቅ፣ አእቅ፣ የተእመቅ፣ መዝ. 112:40)።

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 371) ለመውጣት "ሐ" ደረጃ ይሰጣል (ማለትም፣ ተገቢ ጥርጣሬ)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ከፊተኛው መዝሙር ጋር በምን መልኩ ይዛመዳል?
2. መዝ. 97፡2ሀ የሚገልጸው ምንድነው?
3. መዝ. 97፡4ሀ እና 6 በምን መልኩ ከ "ተፈጥሯዊ ራዕይ" ጋር ይዛመዳሉ?
4. መዝ. 97፡9ለ ላይ "አማልክት" እነማናቸው?
5. ያህዌ ታማኝ ተከታዮቹ እንዲያደርጉ የሚነግራቸው ምንድነው፣ በመጨረሻው አንጓ ላይ?

# መዝሙር 98
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታን ስለ ጽድቁ የማመስገን ጥሪ<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>መዝሙር | የምስጋና መዝሙር፣ ለጌታ ስለ ማዳኑና ፍርዱ | ውዳሴ ወደፊት በምድር ላይ ስለሚመሠረተው የእግዚአብሔር መንግሥት | እግዚአብሔር የምድር ገዥ | የምድር ፈራጅ |
| 98:1-3 | 98:1-3 | 98:1-3 | 98:1-3 | 98:1<br>98:2-3ለ<br>98:3ሐ-4 |
| 98:4-6 | 98:4-6 | 98:4-6 | 98:4-6 | 98:5-6 |
| 98:7-9 | 98:7-9 | 98:7-9 | 98:7-9 | 98:7-8<br>98:9 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ሁለንተናዊው ይዘት፣ እሱም መዝሙር 96 እና 97 ላይ እጅግ የጎላው ቀጥሏል (መዝ. 98:3ለ፣ 4ሀ፣ 7፣ 9ሀ፣ለ)።
1. "በአሕዛብ ፊት፣" መዝ. 98፡2
2. "የምድር ዳርቻዎች ሁሉ አዩ፣" መዝ. 98፡3
3. "ምድር ሁሉ፣" መዝ. 98፡4
4. "ባሕርና... ሞላዋ፣" መዝ. 98፡7
5. "ዓለምም በውስጧም የሚኖሩ፣" መዝ. 98፡7
6. "በምድር ሊፈርድ፣" መዝ. 98፡9
7. "በዓለምም ሊፈርድ፣" መዝ. 98፡9
8. "ለአሕዛብም፣" መዝ. 98፡9

እባክዎትን ልዩ ርዕስ ያንብቡ፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ። እሱም የእኔ ሥነ-መለኮት የተቀናጀ ማዕከል ነው!

ለ. ያህዌ እንደ ንጉሥና ፈራጅ ለመላው ዓለም ይመጣል፣ በተለይም ለእስራኤል። እሱም የሚመጣው ለአባቶች ተስፋ እንደሰጠው ነው (መዝ. 98፡3ሀ)።

ሐ. የመጀመሪያው አንጓ ስድስት የተጠናቀቁ አሉት (የተጠናቀቁ ድርጊቶች) እነርሱም ያህዌ ያደረጋቸው ዝርዝር (ወይም ወደፊት የሚያደርጋቸው፤ በዕብራይስጥ ግሦች የጊዜ ይዘት የሚወሰነው በዐውደ-ጽሑፍ ነው)።
1. ተአምራትን አድርጓል፣ መዝ. 98፡1
2. ድልን አድርጓል፣ መዝ. 98፡1

3. ማዳኑን አስታወቀ፣ መዝ. 98፡2
4. ጽድቁን ገለጠ፣ መዝ. 98፡2
5. ምሕረቱንና እውነቱን አሰበ፣ መዝ. 98፡3
6. የምድር ዳርቻዎች ሁሉ ማዳኑን አዩ፣ መዝ. 98፡3

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 98፡1-3**

**[1]ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋናን አመስግኑ፥**
**እግዚአብሔር ተኣምራትን አድርጎአልና**
**ቀኙ የተቀደሰም ክንዱ ለእርሱ ማዳን አደረገ።**
**[2]እግዚአብሔር ማዳኑን አስታወቀ፥**
**በአሕዛብም ፊት ጽድቁን ገለጠ።**
**[3]ለያዕቆብ ምሕረቱን ለእስራኤልም ቤት እውነቱን አሰበ**
**የምድር ዳርቻዎች ሁሉ የአምላካችንን ማዳን አዩ።**

**98፡1 "ለእግዚአብሔር አዲስ ምስጋናን አመስግኑ፥"** ይህ ቃል ተተኳሪ ነው። አንዱ ሊመለከት ይችላል፣ መዝሙር 95፤ 96፤ እና 98 ለምን አንድ ላይ ተቀራርበው በመዝሙር ላይ መቀመጣቸውን፣ በአዘጋጁ(ጆች)።

"አዲሱ ዝማሬ" የኪዳኑ ሕዝብ ምላሻዊ መልክ አለው፣ ለአምላካቸው ማዳን፣ ምሕረት፣ እና ኃይሉን ማሳየት (መዝ. 98፡1ለ፣ 33:3:40:3፤ 96:1፤ 144:9፤ 149:1፤ ኢሳ. 42:10፤ ራዕ. 5:9፤ 14:3)። ያህዌ በእነርሱ አኳያ ሠርቷል። እሱ እና እሱ ብቻ ነው ኃላፊነቱን የሚወስደው (መዝ. 98፡1ሐ)። ሆኖም፣ መዝ. 37፡40 የሚያሳየው የያህዌ ማዳን/መታደግ ከሰው እምነት እና ታማኝነት ጋር የተያያዘ መሆኑን ነው። ኪዳኑ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን) የያህዌን ሉዓላዊ መነሻነት እና የሰው ልጅን የሚጠበቅ ታዛዥነት፣ ቀጣይነት ያለው ምላሽ ያደባልቃል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መመረጥ/ዕጣ-ፈንታ እና የሥነ-መለኮታዊ ሚዛን አስፈላጊነት)።

በዚህ መዝሙር ጥቅም ላይ የዋሉትን የግሦች ቁጥር ተገንዘብ፣ የድምጽን መፍጠር የሚጠቅሱትን።

1. ዘምሩ፣ መዝ. 98:1 – ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479
2. አስታወቀ፣ መዝ. 98:2 – ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390
3. በደስታ እልል በሉ፣ መዝ. 98:4 – ቢዲቢ 929፣ ኬቢ 1206
4. አቅርቡ፣ መዝ. 98:4 – ቢዲቢ 822፣ ኬቢ 953
5. በደስታ አመስግኑ፣ መዝ. 98:4 – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247
6. ምስጋና ዘምሩ፣ መዝ. 98:4 – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273
7. ምስጋና ዘምሩ፣ መዝ. 98:5 – ከቁ. 6 ጋር ተመሳሳይ
8. በደስታ እልል በሉ መዝ. 98:6 – ከቁ. 3 ጋር ተመሳሳይ
9. ባሕር ተናወጠች፣ መዝ. 98:7 – ቢዲቢ 947፣ ኬቢ 1266
10. ወንዞች አጨበጨቡ፣ መዝ. 98:8 – ቢዲቢ 561፣ ኬቢ 567
11. ተራሮችም ዘመሩ፣ መዝ. 98:8 – ከቁ. 5 ጋር ተመሳሳይ፣ ግን ፒኤል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

▣ **"ተአምራት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተአምራት።

▣ **"እጅ"** ከሥነ-መለኮት አኳያ ከኢሳ. 52፡10 ጋር ትይዩ ነው። ድሉ የእርሱ ነው የእርሱ ብቻ! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ።

▣ **"ድል ነሥቷል"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ ሂፊል የተጠናቀቀ) ፍችው "ማዳን፣" "ድል መንሣት" ነው (ኢሳ. 59:16፤ 63:5)። ድሉ (በዐውደ-ጽሑፋዊው የጊዜ ቅምብብ ሐሳብ ላይ በመመሥረት) ሊያመለክት የሚችለው

1. የፍጥረት መነሻ (ማለትም፣ በውኃው ሁከት ላይ ድል ማድረግ፣ ማለትም፣ መዝ. 65:7፤ 89:9-10፤ 93:34)
2. ዘጸአት/ድል (ኢሳ. 51:9-10፣ ማለትም፣ ቀይ ባሕርና የዮርዳኖስ ወንዝ)
3. አማልክትን ማሸነፍ (ኤሎሂም) የአሕዛብን (መዝ. 2:1፤ 65:7-8)
4. ከስደት መመለስ (ኢሳይያስ 40-45)
5. በክፉ ላይ አጠቃላይ ድል ማድረግ (ማለትም፣ ዘፍ. 3:15፤ ማቴ. 1:21፤ ማርቆስ 10:45፤ 2 ቆሮ. 5:21)

**98፡2 "ጌታ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ **"ደኅንነት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት (ብኪ)።

▣ **"ጽድቅ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ።

▣ **"በአሕዛብ ፊት"** መዝ. 46:10 እና ኢሳ. 52:10። እንደዚያ የሆነው ማየት ስለሚችሉ አይደለም፣ ነገር ግን ሊለወጡ እና ሊዋጁ ስለሚችሉ እንጂ!

**98፡3 "ምሕረቱንና ቸርነቱን ለእስራኤል ቤት"** ይህ የሚያመለክተው ያህዌ ለአባቶች የሰጠውን ተስፋ ነው፣ ከአብርሃም ጀምሮ (ዘፍ. 12:1-3፤ 15:1፤ 17:1-8፤ መዝ. 105:8-15፣42፤ 106:45)።

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቸርነት (ሄስድ) እና

ልዩ ርዕስ፡ ማማን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ።

▣ **"የምድር ዳርቻዎች ሁሉ"** ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ሀ።

ኒዶቲ ገጽ 521፣ ዝርዝር አለው፣ "የምድር ዳርቻዎች ሁሉ" የሚለው ሐረግ እንዴት ጥቅም ላይ እንደሚውል።

1. የያህዌ ስምና ምስጋና – መዝ. 48:10፤ ኢሳ. 42:10
2. እግዚአብሔርን መፍራት – መዝ. 67:7
3. የእግዚአብሔርን ሕግ ማወቅ – መዝ. 59:13
4. የእግዚአብሔር ማዳን – መዝ. 98:3፤ ኢሳ. 49:6፤ 52:10
5. የእሱን የመዋጀት መልእክት – ኢሳ. 48:20፤ 62:11
6. የመሲሐዊውን ንጉሥ ግዛት – መዝ. 2:7፤ ሚክያስ 5:4

ለእኔ ይህ ኢንተርናሽናል፣ ባለ ብዙ ጎሳ (ዘር)፣ ሁለንተናዊ አጽንዖት የ "አሀዳዊነት" አትኩሮትና ፍሬ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት)።

ኤቢ (ገጽ 365-366) ሁለቱን የተጠናቀቁ ግሦች ዳግም ያናብባቸዋል፣ ተተኳሪ ለማድረግ።

1. "አሰበ" – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269 (ይህ እስራኤልን የሚያመለክት ነው)
2. "አዩ" – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157 (ይህ "የምድር ዳርቻዎችን ሁሉ" የሚያመለክት ነው)

ምንም እንኳ ይህ ስሜት ቢሰጥም፣ ከተጠናቀቁት ተለጣጣቂዎች ጋር አይገጥምም እንዲሁም በመዝ. 98፡2 እና 3 መካከል ካለው ትይዩነት። ተተኳሪዎቹ ከቀጣዩ አንጓ ጋር በተሻለ ይገጥማሉ (መዝ. 98፡4-6)።

**መዝሙር ፡ 98፡4-6**

**4 ምድር ሁሉ ሆይ፥ ለእግዚአብሔር እልል በሉ**
**አመስግኑ፥ ደስ ይበላችሁ፥ ዘምሩም።**
**5 ለእግዚአብሔር በመሰንቆ፥**
**በመሰንቆና በዝማሬ ድምፅ ዘምሩ።**
**6 በዋሽንትና በመለከት ድምፅ**
**በንጉሥ በእግዚአብሔር ፊት እልል በሉ።**

**98፡4-6** ይህ አንጓ ስድስት ተተኳሪዎች አሉት፣ ሰዎች ሁሉ የእስራኤልን አምላክ እንዲያመሰግኑ የሚያሳስቡ (መዝ. 98፡3ሀ)። ይህ የእስራኤልን የንግሥና በዓል የሚያንጸባርቅ ሊሆን ይችላል (መዝ. 47፡5-9)።

1. በደስታ እልል በሉ፣ መዝ. 98:4 – ቢዲቢ 929፣ ኬቢ 1206፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
2. አመስግኑ፣ መዝ. 98:4 – ቢዲቢ 822፣ ኬቢ 953፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. በደስታ ዘምሩ፣ መዝ. 98:4 – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ *ፒል ተተኳሪ*
4. ምስጋና ዘምሩ፣ መዝ. 98:4 – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ *ፒል ተተኳሪ*
5. ምስጋና ዘምሩ፣ መዝ. 98:5 – ከቁ. 4 ጋር ተመሳሳይ
6. በደስታ እልል በሉ፣ መዝ. 98:6 – ከቁ. 1 ጋር ተመሳሳይ

እስራኤልና ምድር ሁሉ ተደስተዋል አውጀዋልም፣ የፍጥረትን እና የመዋጀትን አምላክ ታማኝነት፣ ፍትሐዊነት፣ ቅድስና፣ ኃይል፣ እና ጻድቅነት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት)።

ይህ እግዚአብሔር እንዲሆን የፈጠረው ዓለም አይደለም! ይህ አንድ ቀን ወደፊት የሚሆነው ዓለም አይደለም!

**98፡6 "ቀንደ"** ይህ ሾፋር ነው (ቢዲቢ 1051)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ በእስራኤል ጥቅም ላይ የዋሉ ቀንዶች።

**መዝሙር ፡ 98፡7-9**

**7 ባሕርና ሞላዋ፥**
**ዓለምም በእርስዋም የሚኖሩ ይናወጡ።**
**8 ወንዞችም በአንድነት በእጅ ያጨብጭቡ**
**ተራሮች ደስ ይበላቸው፥**
**በምድር ሊፈርድ ይመጣልና።**
**9 ለዓለምም በጽድቅ**
**ለአሕዛብም በቅንነት ይፈርዳል።**

**98፡7-9** የመጨረሻው አንጓ ሦስት ተጽዕኗዊዎች አሉት፣ ሰውኛ ፍጥረትን ለመግለጽ (መዝ. 104:19-22) እንዲሁም ሰዎች የፍጥረትን ጻድቅ ፈራጅ እንዲያመሰግኑ።

1. ባሕርም ትናወጥ – ቢዲቢ 947፣ ኬቢ 1266፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*፣ መዝ. 96:11
2. ምድርም ትዘምር (በትይዩነት ነው አንድምታው ነገር ግን አልተመለከተም)
3. ወንዞችም ያጨብጭቡ – ቢዲቢ 561፣ ኬቢ 567፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
4. ተራራዎች ይዘምሩ – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ *ፒል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*፣ መዝ. 98:4ለ፣ 89:12፤ ኢሳ. 55:12

ቁጥር 1 እና 2 ትይዩ ናቸው፣ ሰዎችን ያመለክታሉ። ቁጥር 3 እና 4 ትይዩ ናቸው፣ ሥጋዊ ፍጥረትን ያመለክታሉ።

**98፡8 "ይመጣልና"** ይህ *ቃል* የድርጊት አንቀጽ ነው። የያህዌ "መምጣት" ሲታሰብ በርካታ ነገሮች አጽንዖት ሊሰጣቸው ይገባል።

1. እሱ ፈጽሞ አይተውም (አይሄድም)። እሱ ዘወትር እዚህ ነው!
2. የእርሱ የተለየ መምጣት ወይም መገኘት ሊሆን የሚችለው
   ሀ. ለበረከት
   ለ. ለፍርድ (እንደዚህ፣ መዝ. 9:7-8፤ 96:13)
3. የእሱ መምጣት የአዲሱን ዘመን ተስፋ ያመጣል (ማለትም፣ የዔድን ኅብረት መመለስ)
4. ይህ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ በሁለቱ የመሲሑ ምጽአቶች ተደግፏል።
   ሀ. የመጀመሪያው በአብዛኞቹ የብሊ ትንቢቶች ተፈጽሟል
   ለ. ሁለተኛው በያህዌ ግዛት ይቀዳጃል

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "የአዲሱ ዝማሬ" ይዘት ምንድነው?
2. መዝ. 98፡1 የሚያመለክተው ድል ምንድነው?
3. መዝ. 98፡3 ከዘፍጥረት 12 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
4. በእስራኤል የአምልኮ ሥርዓት የቀን መቁጠሪያ መሠረት መዝ. 98፡4-6 የትኛውን መደበኛ ሁነት ነው የሚዛመደው?
5. የያህዌን መምጣት መረዳት የምንችልባቸውን የተለያዩ መንገዶች አብራራ።

# መዝሙር 99
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእት** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ጌታን አመስግኑ ስለ ታማኝነቱ<br><br>ኤምቲ መግቢያየለውም | ጌታን አመስግኑ ስለ ቅድስናው | የእግዚአብሔርን ንግሥና ለማክበር ውዳሴ | እግዚአብሔር ሉዓላዊው ንጉሥ | እግዚአብሔር ጻድቁና ቅዱሱ ንጉሥ |
| 99:1-5 | 99:1-3 | 99:1-5 | 99:1-3 | 99:1-2ሀ |
| | | | | 99:2b-3ለ |
| | | | | 99:3ሐ-ሠ |
| | 99:4-5 | | 99:4-5 | 99:4 |
| | | | | 99:5 |
| 99:6-9 | 99:6-7 | 99:6-7 | 99:6-7 | 99:6 |
| | | | | 99:7 |
| | 99:8-9 | 99:8-9 | 99:8-9 | 99:8 |
| | | | | 99:9 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ሦስተኛው አንቀጽ*
4. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

*ሀ. ይህ መዝሙር የያህዌን ገዥነት ያከብራል (መዝ. 93፡1፤ 96፡10፤ 97፡1)፡፡ መዝ. 99፡4 እንኳ፣ ያህዌን ሊጠቅስ ይችላል /ማለትም፣ ኃያሉ ንጉሥ/፡፡ ያህዌ እውነተኛው ንጉሥ ነበር (1 ሳሙ. 8:7፤ መዝ. 47:3፤ 48:2፤ 95:3)፡፡*

ለ. ይህ መዝሙር የሚያንጸባርቀው
1. በምድረ-በዳ የመዞር ጊዜ
   - ሀ. ታቦት (መዝ. 99:1ለ፣ 5ለ)
   - ለ. ሙሴ እና አሮን (መዝ. 99:6ሀ)
   - ሐ. የደመና ዐምድ (መዝ. 99:7ሀ)
   - መ. የሕግ መሰጠት በሲና (መዝ. 99:7ለ፣ሐ)
   - ሠ. ይቅርታ (መዝ. 99:8፣ ዘኍ. 14:20)
2. የጥንቱ የተባበረ መንግሥት (መዝ. 99:6ለ፣ ማለትም፣ ሳሙኤል)
3. መቅደስ በኢየሩሳሌም
   - ሀ. በጽዮን (መዝ. 99:2ሀ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: ጽዮን)
   - ለ. በቅዱሱ ተራራው (መዝ. 99:9ለ)

ሐ. መዝሙር 99:8 ቁልፍ ሥነ-መለኮታዊ ቁጥር ነው፡፡ እሱም መንታዎቹን፣ የማይለያዩትን እውነቶች ያንጸባርቃል

1. የያህዌ በምሕረት የተሞላ፣ ታጋሽ ባሕርይ
2. የሰው ኃላፊነት ለመስማትና ለመታዘዝ (ዘጸ. 34:6-7)

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**_መዝሙር ፡ 99፡1-5_**

**_[1]እግዚአብሔር ነገሠ፥ አሕዛብ ይደንግጡ_**
**_በኪሩቤል ላይ ተቀመጠ፥ ምድር ትናወጥ።_**
**_[2]እግዚአብሔር በጽዮን ታላቅ ነው_**
**_እርሱም በአሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ አለ።_**
**_[3]ግሩምና ቅዱስ ነውና_**
**_ሁሉ ታላቅ ስምህን ያመስግኑ።_**
**_[4]የንጉሥ ክብር ፍርድን ይወድዳል_**
**_አንተ ቅንነትን አጸናህ፥_**
**_ለያዕቆብ ፍርድንና ጽድቅን አንተ አደረግህ።_**
**_[5]አምላካችንን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አድርጉት፥_**
**_ቅዱስ ነውና_**
**_ወደ እግሩ መረገጫ ስገዱ።_**

**99፡1 "እግዚአብሔር ነገሠ"** መዝ. 96፡10 እና 97፡1 ላይ ማስታወሻ ተመልከት። ሁሉም የተጠናቀቁ ናቸው፣ የተጠናቀቁ ድርጊቶችን የሚገልጹ፣ ነገር ግን የዕብራይስጥ ግሦች የጊዜ ቅምብብ መወሰን ያለበት በዐውደ-ጽሑፉ ነው።

▣ **"አሕዛብ ይደንግጡ"** ይህ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 919፣ ኬቢ. 1182፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ) "ምድር ትናወጥ" ከሚለው ጋር ትይዩ ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 630፣ ኬቢ. 680፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፤ ይህ ቃል [ቢ.ዲ.ቢ. 630፣ ኬቢ. 680] እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ. ላይ)። አንድ ላይ በመውሰድ፣ እነርሱ ሌላ ዩኒቨርሳል አጽንዖት ይፈጥራሉ። እዚህጋ የሚያንጸባርቀው የያህዌን ፍርድ (ፍትሕ) ነው (መዝ. 99፡4)።

ሁለቱም ሥጋዊ ፍጥረትና የሰው ልጆች የፈጣሪያቸው ተጽዕኖ ያርፍባቸዋል (ዘጸአት 19፤ መዝ. 77:18፤ ሮሜ. 8:18-25)!

▣ **"በንግሥናው በኪሩቤል ላይ ተቀመጠ"** ግሡ (ቢ.ዲ.ቢ. 442፣ ኬቢ. 444፣ ቃል አንቀጽ) ፍችው "በዙፋኑ ላይ ተቀመጠ" ማለት ነው (1 ሳሙ. 4:4፤ 2 ሳሙ. 6:2፤ 2 ነገ. 19:15፤ 1 ዜና. 13:6፤ መዝ. 80:1፤ ኢሳ. 37:16)። "የኪሩቤል" መጠቀስ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪሩቤል) የሚገልጸው ይህ ሐረግ ዘጸ. 25:22ን ማመልከቱን ነው። ታቦት የያህዌ መገኘት ምድራዊ ስፍራ ነው (ማለትም፣ "የእግሩ መረገጫ፣" መዝ. 99:15ለ፤ 1 ዜና. 28:2፤ ምድር የያህዌ የእግሩ መረገጫ ተብላ ተጠርታለች፣ ኢሳ. 66:1 ላይ፤ መቅደስም የእግሩ መረገጫ በሚል ተጠርቷል፣ መዝ. 132፡7፤ ሰቆ. 2:1 ላይ)። እሱም በኪሩቤል ክንፎች መካከል፣ ከምሕረት መከደኛው በላይ ይኖራል (ማለትም፣ የታቦቱ መከደኛ)። ይህ ልዩ ስፍራ (ማለትም፣ በቅድስተ-ቅዱሳኑ ካለው ታቦት በላይ) እዚያም ሰማይና ምድር፣ የሚታየውና የማይታየው ዓለም የሚገናኙበት!

ልዩ ርዕስ፡ የኪዳን ታቦት

**99፡2 "እግዚአብሔር (ያህዌ) በጽዮን ታላቅ ነው"** ይህ ቅጽል (ቢ.ዲ.ቢ. (ቢ.ዲ.ቢ. 152) ዘወትር ለያህዌ ነው ጥቅም ላይ የሚውለው።

1. አካሉ – ዘዳ. 7:21፤ ነህ. 1:5፤ 8:6፤ 9:32፤ መዝ. 86:10፤ 145:3፤ 147:5፤ ኢሳ. 12:6፤ ኤር. 10:6፤ 32:18፤ ዳን. 9:4
2. ስሙ – ኢያ. 7:9፤ 1 ሳሙ. 12:22፤ 1 ነገ. 8:42፤ 2 ዜና. 6:32፤ መዝ. 76:1፤ 99:3፤ ኤር. 10:6፤ 44:26፤ ሕዝ. 36:23፤ ሚል. 1:11
3. ሥራዎቹ – ዘዳ. 11:7፤ መሳ. 2:7፤ መዝ. 111:2
4. ክብሩ – መዝ. 21:5፤ 138:5
5. ምሕረቱ (ሄሴድ) – 1 ነገ. 3:6፤ 2 ዜና. 1:8፤ መዝ. 57:10፤ 86:13፤ 108:4
6. መልካምነቱ – ነህ. 9:25
7. ርኅራኄው – ኢሳ. 54:7
8. ከአማልክት ሁሉ ታላቅ ነው – ዘጸ. 18:11፤ ዘዳ. 10:17፤ 1 ዜና. 16:25፤ 2 ዜና. 2:5፤ መዝ. 77:13፤ 95:3፤ 96:4፤ 135:5

ስሙ (ቢ.ዲ.ቢ. 152) ደግሞ ለያህዌ ጥቅም ላይ ውሏል ዘዳ. 3:24፤ 5:24፤ 9:26፤ 11:2፤ 32:3፤ መዝ. 105:2 ላይ።

ኤቢ. የሚለው አነጻጻሪው መስተጻምር (ኬቢ. 825፣ ቁ. 1) መዝ. 99፡2ለ ላይ የሚለው ታሳቢ አወዳዳሪ ነው፣ 99፡2ሀ ላይ፣ እሱም የያህዌን ታላቅነት የሚገልጽ፣ በእስራኤል/ይሁዳ ላይ፣ "በአሕዛብ ሁሉ" ላይ/በላይ እንደሆነ ሁሉ (ገጽ 368)። ይህም ከትይዩው ጋር በተሻለ የሚገጥም ይመስላል። እስራኤል ቀዳሚ ነበር፣ ነገር ግን አንዱ ብቸኛው አልነበረም (ማቴ. 28:18-20፤ ሉቃስ 24:46-48፤ ሐዋ 1:8፤ ሮሜ. 1:16)።

▣ **"እርሱም በአሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍ ከፍ አለ።"** ይህ ሐረግ የያህዌን ከፍ ማለት ያሳያል፣ (ቢ.ዲ.ቢ. 926፣ ኬቢ. 1202፣ ቃል አንቀጽ) ከአሕዛብ አማልክት በላይ (ማለትም፣ ከጣዖቶቻቸው፣ መዝ. 97:9፤ 113:4፤ ደግሞም ማስታወሻ ተመልከት ዘጸ. 18:11፤ ዘዳ. 10:17፤ 1 ዜና. 16:25፤ 2 ዜና. 2:5፤ መዝ. 77:13፤ 95:3፤ 96:4፤ 135:5)።

**99፡3 "ታላቅና ግሩም ስምህን ያመስግኑ"** ይህ ሦስተኛው ያልተጠናቀቀ ነው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ (መዝ. 99፡1ሀ፣ለ)።

ለያህዌ "ታላቅ ስም" ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 99፡2 ላይ።

የያህዌ "ግርማዊ (የሚያስፈራ)" ስም ከግሥ ነው (ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ *ኒፉል አንቀጽ*) "መፍራት" ወይም "አስፈሪ" ከሚለው። እሱም ዘወትር ለያህዌ ጥቅም ላይ ይውላል (ዘዳ. 7:21፤ 10:17፣21፤ 28:58፤መዝ. 111:9፤ ሚል. 1:14)።

"ታላቅ" እና "አስፈሪ" የሚሉት ቃላት ዘወትር አንድ ላይ ነው ጥቅም ላይ የሚውሉት፣ ያህዌን ለመግለጽ
(ነህ. 1:5፤ 4:8፤ 9:32፤ ዳን. 9:4)።

"እነርሱም" የሚለው የሚያመለክተው እስራኤላውያን ያልሆኑትን ነው (ማለትም፣ "ሕዝቦች፣" መዝ. 99፡1ሀ፤ "ምድር፣" መዝ. 99፡1ለ፤ "ሕዝቦች ሁሉ፣" መዝ. 99፡2ለ።

▣ **"እርሱ ቅዱስ ነውና"** ይህ መዝ. 99፡5ሐ መደገሙን እና 99፡9ሐ ላይ መጠቀሱን ተገንዘብ፣ ይኸውም ሆን ተብሎ የተደረገ ትይዩ። ለ "ቅዱስ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቅዱስ።

**99፡4** እንደማስበው ይህ ቁጥር ለያህዌ ለራሱ ነው ጥቅም ላይ የዋለው (ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ሀ ተመልከት)። የእርሱ ግዛት (መዝ. 99፡1) ምን ዓይነት ባሕርይ እንዳለው ተገንዘብ።

1. ይወድዳል (ቢዲቢ 12፤ ኬቢ 17፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) ፍትሕን (ቢዲቢ 1048)
2. አጽንቷል (ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 464፣ *ፖለል* የተጠናቀቀ) ቅንነትን (ጽድቅን፣ ቢዲቢ 449)
3. አድርጓል (ቢዲቢ 793፣ ኬቢ 889፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) ፍትሕን (ቢዲቢ 1048) እና ጽድቅን (ቢዲቢ 842፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ)

እነርሱ ሁሉ ሦስት የተጠናቀቁ (ግሦች) እንደሆኑ ተገንዘብ፣ ነገር ግን አአመመቅ፣ አኢመቅ፣ እና አኪጀት የመጀመሪያውን የሚተረጉሙት እንደ የአሁን ጊዜ ሲሆን ቀጣዮቹን ሁለቱን ደግሞ እንደ ሀላፊ ጊዜ ነው። የዕብራይስጥ ግሦች የጊዜ ይዘት መወሰን የሚኖርበት በዐውደ-ጽሑፍ ነው። ስለዚህ፣ እነዚህ የሚገልጹት ያህዌ ማን እንደ ሆነ ነው ወይስ እርሱ ምን እንደሚያደርግ?

"ፍትሕ" እና "ጽድቅ" የሚሉት ቃላት ዘወትር አንድ ላይ ነው ጥቅም ላይ የሚውሉት የነገሥታትን ተገቢ የሆነ አገዛዝ ለማሳየት።

1. ያህዌ ራሱ – መዝ. 99:4፤ ኢሳ. 33:5፤ ኤር. 4:2፤ 9:24
2. ዳዊት – 1 ዜና. 18:14
3. ሰሎሞን – 1 ነገ. 10:9፤ 2 ዜና. 9:8
4. የይሁዳ ነገሥታት – ኤር. 22:3፣15፤ ሕዝ. 45:9
5. የእስራኤል ነገሥታት – አሞጽ 5:9፣24
6. መሲሕ (ማለትም፣ የዳዊት ዘር) – ኢሳ. 9:7፤ 32:1፣16፤ 59:9፣14፤ ኤር. 33:15

**99:5 "አምላካችንን ከፍ ከፍ አድርጉት"** ይህ ከሁለቱ ተተኳሪዎች የመጀመሪያው ነው፣ እሱም የመጀመሪያውን አንጓ የሚዘጋ።

1. ከፍ ማድረግ — ቢዲቢ 926፣ ኬቢ 1202፣ *ፖለል ተተኳሪ*፣ ተመሳሳይ ግሥ መዝ. 99፡2ለ ላይ ጥቅም ላይ ውሏል።
2. ማምለክ ("መስገድ") – ቢዲቢ 1005፤ ኬቢ 295፣ *ሂሽታፌል ተተኳሪ*፣ መዝ. 132:7

ሙሉው የኪዳን መጠሪያ፣ "ጌታ አምላካችን" (ያህዌ ኤሎሂም፣ ዘፍ. 2:4፤ ዘጸ. 20:2) እንዴት ለሦስት ተጨማሪ ጊዜ እንደተደገመ ተገንዘብ፣ መዝ. 99:8ሀ፣ 9ሀ፣ሐ ላይ። ያህዌ በተለየ መልኩ ከአብርሃም ዘርዮች ጋር ይዛመዳል።

1. በጽዮን፣ መዝ. 99:2 (ማለትም፣ መቅደስ)
2. በያዕቆብ፣ መዝ. 99:4ሐ (ማለትም፣ እስራኤል)
3. በሙሴ እና አሮን፣ መዝ. 99:6a (ዘጸአትና የምድረ-በዳው የመዞር ጊዜ)
4. በሳሙኤል፣ መዝ. 99:6ለ (የተባበረው መንግሥት)
5. የእርሱ ሕግ፣ መዝ. 99:7ለ፣ሐ (ዘጸአት 19-20)
6. በቅዱሱ ተራራ፣ መዝ. 99:9ለ

▣ **"የእግሩ መረገጫ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 99፡1ለ ላይ። "መንቀጥቀጥ" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 919) "የእግር መረገጫ" ከሚለው ስም ጋር ተመሳሳይ ነው (ቢዲቢ 919)። ይህ የመከፈቻና የመዝጊያ የድምጽ መቀያየር (ጨዋታ) ሊሆን ይችላል።

**መዝሙር ፡ 99፡6-9**

**6 ሙሴና አሮን በካህናቱ ዘንድ፥**
**ሳሙኤልም ስሙን በሚጠሩት ዘንድ ናቸው።**
**እግዚአብሔርን ጠሩት፥ እርሱም መለሰላቸው።**
**7 በደመና ዓምድም ተናገራቸው**
**ምስክሩንና**
**የሰጣቸውን ትእዛዝ ጠበቁ።**
**8 አቤቱ አምላካችን ሆይ፥ አንተ ሰማሃቸው**
**አቤቱ፥ አንተ ማርሃቸው፥**
**ሥራቸውን ሁሉ ግን ተበቀልሃቸው።**
**9 አምላካችንን እግዚአብሔርን ከፍ ከፍ አድርጉት፥**
**በቅዱስ ተራራውም ስገዱ**
**አምላካችን እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና።**

**99፡6-9** ይህ አንጓ የሚሸፍነው የዘጸአትን፣ የምድረ-በዳ መዞርን፣ ድልን፣ የመንግሥት ተቋም መቋቋምን ነው።

**99:6 "ስሙን በሚጠሩት"** ይህ የሚገልጸው በመቅደስ/በማደሪያ ድንኳን የአምልኮ ድርጊትን ነው (ኢዩኤል 2:32፤ ሐዋ. 2:21፤ ሮሜ. 10:9-13፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት: "መቀበል፣" "ማመን፣" "መናዘዝ/መመስከር፣" እና "መጥራት" ምን ማለት ነው?)። ኤር. 33፡3 ላይ እሱ የሚገልጸው ጸሎትን ነው (ማለትም፣ ግላዊ ግንኙነት)።

እነርሱ እንደሚጣሩ ያህዌም እንደሚመልስ ተገንዘብ (መዝ. 99፡8ሀ)!

**99:7 "የደመና ዓምድ"** ይህ የሚጠቅሰው የተለየ ደመና ነው ("ዓምድ፣" ቢዲቢ 765) የያህዌን አካላዊ መገኘት ይወክላል፣ እሱም ዕብራውያን ባሮችን የሚመራና የሚጠብቅ፣ ግብፅን ለቀው በምድረ-በዳ ሲዞሩ (ዘጸ. 13:21-22፤ 14:19፣24፤ 33:9፣10፤ ዘዳ. 1:33፤ ነህ. 9:12፣19፤ መዝ. 78:14፤ 105:39)።

ይህ ደመና/ዓምድ ተሰወረ፣ እስራኤላውያን የዮርዳኖስ ወንዝን ከተሻገሩ በኋላ፣ ወደ ተስፋይቱ ምድር።

ልዩ ርዕስ፡ ከደመና ጋር መምጣት

▣ **"ምስክርነቶች... ትእዛዝ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ።

▣ **"የሰጣቸውን"** ይህ ቁጥር ስለ እግዚአብሔር ራዕይ ነው (ማለትም፣ "ተናገራቸው" ... "ሰጣቸው") እና የእርሱ ሕዝብም ታዛዥነት (መዝ. 99፡7ለ፣ ማለትም፣ "ጠበቁት")።

"እነርሱ" የሚለው መዝ. 99፡7 ላይ ያለው የሚጠቅሰው ሙሴን (ዘጸ. 33፡9) እና አሮንን ይመስላል (ዘኍ. 12፡4-8)። እሱም ደግሞ እስራኤላውያንን ሁሉ ሊጠቅስ ይችላል (ዘጸአት 19-20)።

ይህም የክርስትና/ይሁዲነት ማዕከላዊ ጉዳዮች አንደኛው ነው! አንዱ እውነተኛው አምላክ ራሱን እንዴት ይገልጻል

1. በፍጥረት
2. በተስፋዎች
3. በድርጊቶች
4. ቁ. 1-3 በብኪ ላይ መዝግበዋቸዋል
5. በልጁ
6. ቁ. 5 በአኪ ላይ መዝግቧቸዋል

ልዩ ርዕስ፡ ተመስጦ

ልዩ ርዕስ፡ ማብራራት (ማብራት)

ሦስቱን የቪዲዮ ስብከቶች በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ላይ ይመልከቱ www.freebiblecommentary.org በመግቢያ አንቀጹ ላይ፣ በመክፈቻው-ገጽ።

1. ብኪን ለምን እንደማምን
2. አኪን ለምን እንደማምን
3. ክርስትና እውነት ነውን?

**99፡8 "አንተ ሰማሃቸው"** ይህ ከጸሎት ጉዳይ ጋር ይዛመዳል። ሦስት ልዩ ርዕሶች አሉኝ (ከታች ተመልከት) ይሄንን ጉዳይ የሚመለከቱ። "እነርሱም"፣ "እነርሱ" የሚለውን አጠቃቀም ይከተላል መዝ. 99፡6 ላይ። ሁለቱም የሚያመለክቱት ከህነታዊ ጸሎትን ነው፣ የሙሴን፣ አሮንን፣ እና ሳሙኤልን፣ ታላላቆቹ የብኪ ማላጆች (ኤር. 15፡1)።

1. ሙሴ – ዘጸ. 32:9-14፣31-32፤ ዘኍ. 14:13-19፤ 21:7፤ ዘዳ. 9:18-20፣25-29፤ መዝ. 106:23
2. ሳሙኤል – 1 ሳሙ. 7:5፣8-9፤ 12:19፣23

ልዩ ርዕስ፡ የሰመረ ጸሎት

ልዩ ርዕስ፡ የምልጃ ጸሎት

ልዩ ርዕስ፡ ጸሎት፣ ያልተወሰነ ሆኖም የተወሰነ

የእግዚአብሔር ምላሽ ሁለት መልኮችን ወስዷል።

1. ይቅርታ (ማለትም፣ ዘጸ. 34:6-7፤ ዘኍ. 14:17-19፤ ነህ. 9:17፤ መዝ. 78:32፤ 86:15፤ 103:6-14)
2. ክፉ ድርጊታቸውን የሚበቀል (ማለትም፣ ዘጸ. 32:28፤ ዘኍ. 20:12፤ መዝ. 95:11፤ 107:12)

እነዚህ አንድ ላይ የሚሄዱ ናቸው (መዝ. 99፡7ለ) ምክንያቱም መታዘዝ ዓይነተኛ ነገር ስለሆነ። ፍርድ ሁለቱንም ነው፣ ቅጣት (ማለትም፣ ስደት) እና መዋጀት (ዕብ. 12:5-13)። ኒዶቲ፣ ቅጽ. 3፣ ገጽ. 155 ታላቅ መግለጫ አለው፣ "ምሕረት እና በቀል፣ ሕጋዊነት እና ጸጋ፣ ፍቅር እና ቁጣ በያህዌ ተቃርኖ አይደሉም።" እነርሱ የሚያንጸባርቁት የጸጋ ኪዳን ከሰው ምላሽ ጋር ያለውን የተቃርኖ ሚዛን ነው። ለሙሉ የ "ቅጣት" ማብራሪያ ኒዶቴ ቅጽ 4፣ ገጽ 1140-1149 ተመልከት።

**99፡9** አኪመቅ መዝ. 99፡9 የተነጠለ አንጓ አለው፣ እናም ሊሆን ይችላል፣ ምክንያቱም ሁለት ተተኳሪዎች ላይ ስለሚለወጥ፣ ለእስራኤል የተነገሩ።

1. ጌታ አምላካችንን ከፍ አድርጉት – ቢዲቢ 926. ኤልቢ 1202፣ *ፖለል ተተኳሪ*፣ መዝ. 99:5
2. በቅዱሱ ተራራው ላይ ስገዱለት (ማለትም፣ መቅደስ) – ቢዲቢ 1005፣ ኬቢ 295፣ *ሂሽታፌል*፣ መዝ. 99:5

ሆኖም፣ ሆን ተብሎ የተዋቀረውን አንዳ አንድን ተገንዘቡ፣ በእነዚህ ተመሳሳይ ተተኳሪዎች የተጠናቀቀውን (መዝ. 99፡5) እና ከዚያም አንዳ ሁለት፣ በተመሳሳይ ተተኳሪዎች የተጠናቀቀውን። የአንዳ ምድቦች ተመስጦአዊ አለመሆናቸውን አስታውስ። ዘመናዊዎቹ ምዕራባዊ ሰዎች ዘወትር የብኪን ቅኔ የሚተነትኑት የእኛን ባህልና ጽሑፋዊ ሞዴሎችን በሚያንጸባርቅ መልኩ ነው፣ በጥንታውያኑ የዕብራይስጥ እና ጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ሞዴሎች ሳይሆን። ይህም በተለይ በውጋሪት ሞዴሎች እውነት ነው።

▣ **"አምላካችን እግዚአብሔር ቅዱስ ነውና።"** ተመሳሳይ ሐረግ መዝ. 99፡5ን የዘጋው።

አንዳንድ የእንግሊዝኛ ቅጅዎች የዚህን ባለ ሦስትዮሽ ድግግሞሽ ሐረግ የሚመለከቱት (መዝ. 99:3፣5፣9) ጸሐፊው መዝሙሩን በሦስት አንዳዎች እንደሚከፋፍልበት መንገድ ነው (አኪጀት፣ አእቅ)፤ ጀፒኤስኦኤ አራት አለው (መዝ. 99፡1-3፣ 4-5፣ 6-8፣ 9)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የኪዳኑን ታቦት ጠቀሜታ ግለጽ።
2. ይህ መዝሙር፣ እንደ ቀዳሚው ሁሉ፣ ዩኒቨርሳላዊ ይዘት (ነገር) አለውን?
3. መዝ. 99፡4 የሚናገረው ስለ ሐሳባዊ ዳዊታዊ ንጉሥ ነውን ወይስ ስለ ያህዌ ስለ ራሱ?
4. ሙሴ፣ አሮን፣ እና ሳሙኤል መዝ. 99፡6 ላይ ለምን ተጠቀሱ?
5. ያህዌ ሁለቱንም እንዴት ሊሆን ይችላል፣ ይቅር ባይና ተበቃይ?

# መዝሙር 100
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ሰዎች ሁሉ አምላክን እንዲያመሰግኑ ይጠራሉ<br>ኤምተ መግቢያ<br>የምስጋና መዝሙር | የምስጋና መዝሙር፣ ጌታ ለሕዝቡ ካለው ታማኝነት | የውዳሴ ጥሪ አሕዛብ ሁሉ ጌታን እንዲያመሰግኑት | የምስጋና ዝማሬ | የምስጋና ጥሪ |
| 100:1-3 | 100:1-3 | 100:1-2 | 100:1-2 | 100:1-2 |
| | | 100:3 | 100:3 | 100:3 |
| 100:4-5 | 100:4-5 | 100:4 | 100:4 | 100:4 |
| | | 100:5 | 100:5 | 100:5 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

9. የመጀመሪያው አንቀጽ
10. ሁለተኛው አንቀጽ
11. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ አጭር መዝሙር ሰባት ተተኳሪዎች አሉት፣ የእግዚአብሔርን ሕዝብ የሚመለከቱ።
6. እልል በሉ፣ መዝ. 100፡1 – ቢዲቢ 929፣ ኬቢ 1206፣ *ሂፊል* መዝ. 47፡1፤ 95፡1፡2
7. አገልግሉ፣ መዝ. 100:2 – ቢዲቢ 712፣ ኬቢ 773፣ *ቃል*፣ ዘጸ. 3:12፤ 4:23፤ ዘዳ. 6:13፤ 1 ሳሙ. 7:3፤ 1 ዜና. 28:9
3. ኑ፣ መዝ. 100:2 – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል*
4. እወቁ (ማለትም፣ "በአምልኮ ጽናት" በሚል መልኩ)፣ መዝ. 100:3 – ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ *ቃል*
5. ግቡ፣ መዝ. 100:4 – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል*፣ መዝ. 96:8
6. ምስጋና አቅርቡ፣ መዝ. 100:4 – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል*
7. ባርኩ፣ መዝ. 100:4 – ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ *ፒል*

ለ. ብቸኛው ግሥ (የተጠናቀቀ) ተተኳሪ ያልሆነ፣ መዝ. 100፡3ለ ነው፣ እሱም ያህዌ እስራኤልን እንደመረጠና እንዳዳነ የሚገልጽ (ማለትም፣ ዘፍ. 12:1-3፤ 15:12-21)።
1. እሱ ፈጠረን – መዝ. 95:6፤ 119:73
2. እስራኤል የእርሱ መንጋ ነው – መዝ. 23:1፤ 74:1፤ 95:7፤ ኢሳ. 40:11፤ ኤር. 31:10፤ ሕዝ. 34:31 (ደግሞም መሲሐዊ ማጣቀሻ፣ ሕዝ. 34:23፤ ሚክያስ 5:4፤ ዘካርያስ 11፤ ዮሐንስ 10:11፡14-16)

ሐ. ምንም ግሣዊ የለም መዝ. 100፡5 ላይ። "የይሆናል" ግሥ ሊደረግለት ይገባል። መዝሙር 3፡ለ፡ሐ እና 5 ያህዌን ራሱን እና የመዋጀት ሥራውን ይገልጻሉ።

መ. አንዳንድ ሊቃውንት (ማለትም፣ ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ) የሚያምኑት ይህ መዝሙር የመዝጊያ ቡራኬ እንደሆነ ነው፣ "የንግሥና መዝሙራት" (ማለትም፣ መዝሙር 93፤95-99)። "ንጉሥ" የሚለው ቃል ጥቅም ላይ አልዋለም፣ ነገር ግን መዝ. 100፡3ለ-ሐ የእርሱ ጠቃሽ ሊሆን ይችላል።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 100፡1-3**

[1]ምድር ሁሉ፥ ለእግዚአብሔር እልል በሉ፥
[2]በደስታም ለእግዚአብሔር ተገዙ፥
በሐሤትም ወደ ፊቱ ግቡ።
[3]እግዚአብሔር እርሱ አምላክ እንደ ሆነ እወቁ
እርሱ ሠራን እኛም አይደለንም
እኛስ ሕዝቡ የማሰማርያውም በጎች ነን።

**100፡1** መዝሙራቱ በመደበኛነት የሚገልጹት የእስራኤልን አምላክ ሁለንተናዊ ገጽታ ነው። እሱ ብቸኛው እውነተኛ አምላክ፣ ፈጣሪ፣ መጋቢ፣ ተቤዢ ነው (መዝሙር 33፤ 47፤ 98)።

ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 852) የሚለው "ምድር ሁሉ" እያንዳንዱን የቅኔውን ስንኝ መረዳት ይኖርበታል መዝ. 100፡2-4።

**100፡2** ከያህዌ አኳያ እንደ አንዱና ብቸኛው አምላክ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት) እነርሱ

1. በደስታ ያገለግሉታል ዘዳ. 12:11-12፤ 28:47
2. በደስታ ዝማሬ ወደ ፊቱ ይቀርባሉ፣ መዝ. 66:1፤ 81:1፤ 95:2

እነዚህ ሁለቱም ተተኳሪዎች (ደግሞ፣ መዝ. 100፡4) የመቅደስ አምልኮን ይጠቅሳሉ።

▣ **"በደስታ ዝማሬ"** ይህ አንስታይ (ሴቴ) ስም (ቢዲቢ 943) የሚያመለክተው የደስታ እልልታን ነው (ማለትም፣ ኒዶቲ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 1128) ወይም "የደስታ ልቅሶ፣" ኢዮብ 3:7፤ 20:5፤ መዝ. 63:5።

**100፡3 "እግዚአብሔር እርሱ አምላክ ነውና"** ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ ለያህዌ የተለየነት (ዘጸ. 8:10፤ 9:14፤ ዘዳ. 4:35፣39፤ 1 ነገ. 18:39፤ መዝ. 46:10)።

▣ **"እርሱ ሠራን"** ይህ የሚያመለክተው መጠራትና ተስፋን ነው (ዘጸአትን ጨምሮ፣ ዘፍ. 15፡12-21) ለአብርሃምና ለዘሮቹ (ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተምልከት፣ ለ)።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀት፣**
**አኢመቅ፣ LXX፣**
**ፔሺታ** **"እኛም አይደለንም"**
**አኪጀት፣ አእቅ፣**
**ጀፒኤስኦኤ፣ የተእመቅ፣**
**ቫልጌት** **"እኛም የእርሱ ነን"**

የመጀመሪያው አማራጭ ኤምቲን ተከትሎ ነው (*ኬቲቭ*)። ሁለተኛው የማሶረቲክ ሊቃውንት አስተያየት ነው፣ ኤምቲን ያቀነባበሩት (ቄሬ)። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 373) ለቄሬ "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ)።

ችግሩ ያለው "አይደለንም" የሚለው፣ "እርሱ" ለሚለው መስተጻምር ወይም መስተዋድድና አሉታዊ መሆኑ ላይ ነው። ሁለቱም በሚነበቡበት ጊዜ ተመሳሳይ ድምጽ አላቸው።

**መዝሙር ፡ 100፡4-5**

[4]ወደ ደጆቹ በመገዛት፥
ወደ አደባባዮቹም በምስጋና ግቡ
አመስግኑት፥ ስሙንም ባርኩ
[5]እግዚአብሔር ቸር፥
ምሕረቱም ለዘላለም፥
እውነቱም ለልጅ ልጅ ነውና

**100፡5** ያህዌ ባሕርዩ እንዴት እንደሆነ ተገንዘብ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት)።

1. መልካም፣ መዝ. 106:1፤ 117:1፤ 118:1፣29፤ ኤር. 33:1፣
2. በምሕረት የተሞላ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቸርነት (ሄሰድ)
3. ዘላለማዊ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (ኦላም)
4. ታማኝ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብሊ
5. ለሁሉ በጊዜ ሁሉ ውስጥ
   ሀ. እስራኤልም ቢሆን ወይም
   ለ. ሰዎች ሁሉ በእርሱ የሚታመኑ

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

11. ይህ መዝሙር ለማን ነው የተመለከተው?
12. ምን ዓይነት የመፍጠር ድርጊት ነው መዝ. 100፡3ለ የሚጠቅሰው?
13. መዝ. 100፡5 ላይ ያሉትን ዋነኞቹን ሥነ-መለኮታዊ ቃላት ዘርዝር፣ ግለጽም።

# መዝሙር 101
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእት** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የመዝሙረኛው ማጽኛ ለጻድቅ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር | ቃል የተገባ ታማኝነት ለጌታ | የንጉሥ ቃል መግባት በፍትሕ ለመግዛት | የንጉሥ ተስፋ | ሁነኛ ገዥ |
| 101፡1-5 | 101፡1 | | | |
| | 101፡2 | 101፡1-2ለ | 101፡1-2ለ | 101፡1-2ለ |
| | 101፡3-4 | 101፡2ሐ-3ለ | 101፡2ሐ-5 | 101፡2ሐ-3ለ |
| | 101፡5 | 101፡3ሐ-4 | | 101፡3ሐ-4 |
| 101፡6-8 | 101፡6-8 | 101፡5 | | 101፡5 |
| | | 101፡6 | 101፡6 | 101፡6 |
| | | 101፡7 | 101፡7-8 | 101፡7 |
| | | 101፡8 | | 101፡8 |

### **የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. የመጀመሪያው አንጓ የሚጀምረው በሦስት ተጓዳኞች ነው (መዝ. 101፡1-2፣ ማለትም፣ *የብኪ ትንታኔ መመሪያ*፡ ገጽ 451)።
1. እዘምራለሁ – ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ *ቃል*
2. ምስጋና እዘምራለሁ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 372፣ *ፒል*
3. አተኩራለሁ – ቢዲቢ 968፣ ኬቢ 1328፣ *ሂፊል*

አአመመቅ አንጓውን ይቀጥላል እስከ መዝ. 101፡5 ድረስ። ሌሎች በርካታ ተጨማሪ "እኔ… ራለሁ" የሚሉ መግለጫዎች፣ እነርሱም በተጓዳኝ ጥቅም ላይ የዋሉ።
1. እራመዳለሁ ... መዝ. 101፡2 – ቢዲቢ 229፣ ቢኬ 246
2. አዘጋጃለሁ. . .፣ መዝ. 101፡3 – ቢዲቢ 1011፣ ኬቢ 1483፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
3. እጠላለሁ መዝ. 101፡3 – ቢዲቢ 971፣ ኬቢ 1338፣ *ቃል* የተጠናቀቀ (ግን ባልተጠናቀቀ ተለጣጣቂነት)
4. አውቃለሁ. . .፣ መዝ. 101፡4 – ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
5. እጠፋዋለሁ. . .፣ መዝ. 101፡5 – ቢዲቢ 856፣ ኬቢ 1035፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ
6. እታገሣለሁ፣ መዝ. 101፡5 – ቢዲቢ 407፣ ኬቢ 410፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ

ላስተባባይነት ያህል፣ ሌሎች ሊቃውንት እነዚህን ግሦች የሚመለከቱት፣ ያለፈ ድርጊትን እንደሚጠቅሱ ነው (ኤቢ፣ ቅጽ 17ሀ፣ ገጽ 4)። እንደሚመስለኝ፣ ቀዳሚዎቹ ግሦች ያህዌ በሚመጣ ጊዜ መዝሙረኛው ምን እንደሚያደርግ ነው (መዝ. 100፡2ለ) ከመልካም የኪዳን ታማኝነቱ አኳያ።

ለ. ይህ አንጓ (መዝ. 101፡1-5) የሚያመለክተው የመዝሙረኛውን እምነት እና ታማኝነት ለማጽናት ነው፣ ለያህዌና ለእርሱው መገለጥ።
1. እሱ ስለ ያህዌ ቸርነት ይዘምራል (ማለትም፣ ሄሰድ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቸርነት [ሄሰድ]፤ ከመዝ. 101፡2-5 የተነሣ፣ እነዚህ ቀዳሚዎቹ ሁለቱ የመዝሙረኛውን ታማኝነት እና ደግነት የሚገልጹ ናቸው። እነዚህ ሁለቱ ስሞች ዘወትር የሚገልጹት ያህዌን ነው። ንጉሡ የያህዌን ባሕርይ ማንጸባረቅ ይኖርበታል)።
2. እርሱ ስለ ያህዌ ፍርድ ይዘምራል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፈራጅ፣ ፍርድ፣ ፍትሕ)

3. እሱ የሚኖረው ያለ ነውር ነው
   ሀ. ለ “ያለ ነውር፣” ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ነውር የሌለበት፣ ንጹሕ፣ ያለ ነቀፋ
   ለ. ለ “መንገድ፣” የዌብሳይት ማስታወሻዎችን ተመልከት ዘዳ. 8፡6 እና 10፡20፤ መዝ. 1፡1፤ ለሚዛመድ ቃል “መንገድ” (ቢዲቢ 73) ዌብ ሳይት ማስታወሻ ተመልከት ኢሳ. 2፡3 ላይ
4. እሱ በልቡ ቅንነት ይራመዳል (ቢዲቢ 1070)
5. የማይረባ ነገርን አያስቀምጥም (ቢዲቢ 116) በዓይኖቹ ፊት
6. ከቀና የሚጠመዘዙትን ይጠላል (ያልተለመደ ስም፣ ሁለት ጊዜ ብቻ በብኪ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ቢዲቢ 962፣ ሆሴዕ 5፡2)
7. የእነርሱ ክፉ እንዲሆን አይፈቅድም (ማለትም፣ ቁ. 6) በእርሱ ላይ እንዲጣበቅ
8. ክፉን ፈጽሞ አያውቅም
9. በስውር የሚያሴሩትን እነርሱን ያጠፋል/ዝም ያሰኛል
10. እሱም ፈጽሞ አይታገሥም
    ሀ. የኩራት አስተያየት ያላቸውን
    ለ. ትዕቢተኛ ልብ ያላቸውን

ሐ. ሁለተኛው አንጓ ይቀጥላል፣ የመዝ. 101፡1-5ን አጽንዖት። ይህም የመዝሙረኛውን መልካም የሕይወት ስልት እና ክፉን መጻየፉን ይገልጻል።
1. አዎንታዊ (መዝ. 101፡6)
   ሀ. እሱም የምድሪቱን ታማኝ ያውቃል
   ለ. እነርሱም አንድ ላይ እንዲኖሩ ይመኛል
   ሐ. እሱም ነውር የሌለበት ሕይወት የሚኖሩትን ይፈቅዳል (መዝ. 101፡6ለ) ከእርሱ ጋር ይሠሩ/ያገለግሉ ዘንድ
2. አሉታዊ (መዝ. 101፡7-8)
   ሀ. ማሳት የሚያደርጉትን ከእርሱ ጋር ይኖሩ ዘንድ አይፈቅድላቸውም
   ለ. ሐሰት የሚናገሩትን ከእርሱ ጋር እንዲሠሩ/እንዲያገለግሉ አይፈቅድላቸውም
   ሐ. እሱም ዘወትር የምድሪቱን ኃጢአተኞች ያጠፋል/ዝም ያሰኛል
   መ. እሱም መዝሙረኛው “ንጉሥ” ነው የሚሉትን ይቆርጣል

መ. የታማኝ ተከታዮች ተቃራኒዎች ባሕርያት እንዴት እንደተሳሉ ተገንዘብ
1. ጣዖት አምላኪዎች፣ መዝ. 101፡3ሀ
2. ከሀዲዎች፣ መዝ. 101:3ለ
3. ተቃዋሚ ልብ መዝ. 101:4ሀ
4. በስውር የሚያሙ፣ መዝ. 101:5a
5. የኩራት አስተያየት፣ መዝ. 101:5ለ
6. ትዕቢተኛ ልብ፣ መዝ. 101፡5ለ
7. ማሳሳትን ይፈጽማል፣ መዝ. 101፡7ሀ
8. ሐሰትን ይናገራል፣ መዝ. 101፡7ለ
9. ኃጢአተኛው፣ መዝ. 101፡8ሀ
10. በደልን የሚፈጽሙ፣ መዝ. 101፡8ለ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 101፡1-5**

**1 አቤቱ፥ ምሕረትንና ፍርድን**
**እቀኝልሃለሁ።**
**2 እዘምራለሁ፥ ንጹሕ መንገዱንም አስተውላለሁ**
**ወደ እኔ መቼ ትመጣለህ?**
**በቤቴ መካከል በልቤ ቅንነት እሄዳለሁ።**
**3 በዓይኔ ፊት ክፉን ነገር አላኖርሁም**
**ሕግ ተላላፊዎችን ጠላሁ።**
**4 ጠማማ ልብም አልተጠጋኝም**
**ክፉ ከእኔ በራቀ ጊዜ አላወቅሁም።**
**5 ባልንጀራውን በቀስታ የሚያማን እርሱን አሳደድሁ**
**በዓይኑ ትዕቢተኛ የሆነውና ልቡ የሚሳሳው ከእኔ ጋር አይተባበርም።**

**101፡1 “ምሕረትና ፍርድ”** ለ “ምሕረት” ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት (ሄሰድ)። ለ “ፍርድ” ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፈራጅ፣ ፍርድ፣ ፍትሕ።

▣ **“ጌታ ሆይ”** ይህ የኪዳን መጠሪያ ነው ለእስራኤል አምላክ (ያህዌ)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

**101፡2 “ንጹሕ”** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ነውር የሌለው፣ ንጹሕ፣ ያለ ነቀፋ።

◘ ***"ወደ እኔ መቼ ትመጣለህ?"*** ይህ ሐረግ ተተርጉሟል "መቼ አገኘዋለሁ?" በሚል በጄፒኤስአኤ። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 373) ኤምቲን ይደግፋል በ "ለ" ደረጃ (መጠነኛ ጥርጣሬ)።

እሱም ብኪን፣ የሙሴን ድርጊት-ተኮር ኪዳንን ያንጸባርቃል። እሱም ዘወትር "ሁለቱ መንገዶች" በሚል ይጠራል (መዝሙር 1፤ ዘዳ. 30:1፣15-20፤ ኤር. 17:5-8)። እሱ "የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ" ነው፣ ምድቡም የሚጠራባቸው ቃላት

1. የተባረከ (መዝ. 1:1፤ ማቴዎስ 7)
2. የተረገመ (ዘዳግም 27-28)
3. የተከለ ሕይወት፣ ፍሬአማ የሆነ ወይም የሞተ

ብልጽግና ከእግዚአብሔር እንደሆነ ቀጥተኛ ስጦታ ተደርጎ ይታይ ነበር፣ ለኪዳን መታዘዝ፣ ነገር ግን ችግሮች ነበሩ፣ ከኃጢአት የሆነ ቀጥተኛ ውጤት (ኢዮብ፤ መዝሙር 73)። ይህ የብኪ ሥነ-መለኮታዊ አተያይ በአኪ መገለጥ መሻሻል ይኖርበታል። እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ለእኛ ነው፣ በእርሱ ማንነት ላይ በመመሥረት! ኢየሱስ የመጣው ለሁሉም ነው፣ ለጥቂቶች ብቻ ሳይሆን። ብኪ የሚያተኩረው በደህው፣ በተገለለው፣ እና በማኅበረሰቡ ውስጥ ደካማ በሆነው ላይ ነው፣ እርሱ ለሁሉም ያለውን ፍቅር ማስረገጫ ሥነ-መለኮታዊ መንገድ፣ በውጫዊ ለተባረኩት ብቻ ሳይሆን! እሱ በክርስቶስ መጥቷል! የእርሱም ፍቅር ተቀባይነት ማግኘት የሚኖርበት በንስሐ፣ በእምነት፣ በመታዘዝ፣ በአገልግሎት፣ እና በትዕግሥት ነው።

◘ **"በቤቴ መካከል"** ይህ ሐረግ አሻሚ ነው። እሱም ሊያመለክት የሚችለው

1. አሕዛብን (መዝ. 101:7፣ ማለትም፣ መዝሙረኛው እንደ ንጉሥ)
2. የአገር ውስጥ ስፍራ
3. ኅብረተሰብ

መዝሙረኛው ያስረግጣል፣ አንድም አሁን ያለበትን ወይም ፊት ለያህዌ የነበረውን የኪዳን ታዛዥነት፣ በሙሴ። መዝ. 101:3 የተገለጹት እነርሱ፣ ሆን ብለው ኪዳኑን በመደጋገም የሚጥሱ ናቸው (ያልተጠናቀቀ)።

"ቤት" የሚለው ቃል ቢዲቢ 108፣ ጥቅም ላይ የዋለው ለንጉሥ ቤተ-መንግሥት ነው 1 ነገ. 4:6፤ 16:9፤ ኢሳ. 22:15። ይህም ደረሲው ንጉሥ ነበር የሚለውን ሐሳብ ያጠናክራል።

**101:3** ይህ ቁጥር የሚገልጸው ከእምነት መከዳትን ነው። ቃሉ የተተረጎመው "መውደቅ" በሚል ሲሆን (ቢዲቢ 962፣ ኬቢ 750) የሚከሰተውም እዚህጋ ብቻና ሆሴዕ 5:2 ላይ ነው። ኬቢ የሚለው "ማፈንገጥ" ወይም "መተላለፍ" ነው (LXX)። ይህ አስቸጋሪ ጽንሰ-ሐሳብ ነውነገር ግን በቅዱስ ቃሉ የተደገመ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ክህደት። በአብዛኛው የእስራኤል ታሪክ ውስጥ ጥቂት ሕዝቦቿ ብቻ ናቸው ታማኝ ተከታዮች።

◘ **"የማይረባ ነገር"** ይህ ስም (ቢዲቢ 116) ኋላ ላይ ለሰይጣን መጠሪያ ከሆነው የመጣ ነው፣ ቢሊያል፣ የወጣበት። የእርሱ መሠረታዊ ፍቺ "የማይረባ፣" "ለምንም ነገር የማይበጅ፣" "ወራዳ" ነው። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ እሱ የሚያመለክተው ጣዖት አምላኪነትን ነው (ኤቢ፣ ቅጽ 17ሀ፣ ገጽ 61)።

ማስታወሻውን ተመልከት ከዘዳ. 13:13።

> **ዘዳ. 13:13 "ምናምንቴ ሰዎች"** ይህ በጥሬው ፍችው "የቢሊያል ልጆች" ነው (ቢዲቢ 116) የዕብራይስጡ ቃል ፍችው "የማይረባው" ወይም "ለምንም ነገር የማይበጅ" ማለት ነው (መሳ. 19:22፤ 20:13፤ 1 ሳሙ. 10:27፤ 30:22፤ 1 ነገ. 21:10፣13፤ ምሳ. 6:12)። በአኪ ጊዜ ቢሊያል የሰይጣን ተመሳሳይ ሆነ (2 ቆሮ. 6:15)። ሥነ-መለኮታዊ መሻሻል አለ፣ በቅዱስ ቃሉ ላይ፣ እዚያም ክፉው በሰውኛ ዘይቤ የተጠቀሰበት።

ልዩ ርዕስ፡ አካላዊው ክፉ

**101:4 "ክፉ"** ክፉ (ቢዲቢ 948 II)፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ፣ የያህዌን የተገለጠ ፍቃድ ሆን ብሎ መጣስ ነው። ክፉ ሰዎች መዝ. 101:3ለ፣ 5ሀ፣ 6 ላይ በመመልከታቸው ምክንያት፣ ይህም ደግሞ ክፉ ሰውን የሚጠቅስ ይመስለኛል (አአመቅ፣ አዲሱ በርክሌይ ቅጅ)። የእኔን ማስታወሻ ተመልከት፣ ዘዳ. 30:15-20 ፄሳይት መስመር፣ www.freebiblecommentary.org.

**101:5 "አጠፋለሁ"** ግሡ (ቢዲቢ 856፣ ኬቢ 1035፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ* [አምናለሁ፣ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ መዋሉ]) ፍችውም "መደምሰስ፣" ወይም "መፍጀት" በዕብራይስጥ፣ በዓረብኛ ግን ፍችው "ዝም ማሰኘት" ነው (አኢመቅ)። ይኸኛው የሥር ፍች ይህንን ዐውደ-ጽሑፍ በተሻለ ይገጥማል። እሱም የሚያሳየው የምሥጢር ውሸቶች/ሐሜቶች ጸጥ እንደሚሰኙ ነው (የተእመቅ)።

አንድ ቀን ፍትሕ ይመጣል! በክርስቶስ መጥቷል (ማቴ. 3:2፤ 4:17) እናም አንድ ቀን በምድር ሁሉ ላይ ይቀዳጃል (ማቴ. 6:10፤ ዮሐንስ 14:1-3፤ ራዕ. 11:15)።

◘ **"እታገሣለሁ"** ኤምቲ (ቢዲቢ 407፣ ኬቢ 410፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) ተናባቢዎች፣ יכל፣ በLXX የሚተረጎሙት እንደ אכל (ቢዲቢ 37) ነው። ይህ ማሻሻያ በየትኞቹም ዋነኞች የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ድጋፍ አላገኘም፣ ከአእመቅ በስተቀር፣ የተእመቅ ን ተከትሎ። "መታገሥ" ወይም "መቻል" የ "ማጥፋት" ወይም "ዝም የማሰኘት" ትይዩ ናቸው።

### *መዝሙር ፡ 101:6-8*

**[6]ከእኔ ጋር ይኖሩ ዘንድ ዓይኖቼ በምድር ምእመናን ላይ ናቸው**
**በቀና መንገድ የሚሄድ እርሱ ያገለግለኛል።**
**[7]ትዕቢትን የሚያደርግ በቤቴ መካከል አይኖርም**
**ዓመፅን የሚናገር በዓይኔ ፊት አይቀናም።**
**[8]ዓመፃ የሚያደርጉትን ሁሉ ከእግዚአብሔር ከተማ አጠፋቸው ዘንድ፥**
**የምድርን ኃጢአተኞች ሁሉ በማለዳ እገድላቸዋለሁ።**

**101፥6** በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ሁለቱንም መዝ. 101፥5 እና 6 የተለያዩ አንጓዎች ያደርጓቸዋል (አየተመት፣ አኢመቅ)። ይህም ሊሆን የቻለው መዝ. 101:3-4፣ 5 (እና 7) ንጉሡ የማይቀበለውን በመግለጻቸው ምክንያት ሲሆን መዝ. 101፥6 ደግሞ ንጉሡ የሚቀበላቸውን ስለሚገልጽ ነው። እነዚህ የታመኑ ተከታዮች ዓይነት ናቸው፣ እንደ ንጉሡ እንደ ራሱ የሆኑ (መዝ. 101:1-2)።

**101፥7 "በፊቴ"** ይህ አወቃቀር ቢዲቢ 617 እና ቢዲቢ 744 ተደግሟል ከመዝ. 101:3ሀ። ይህ ሐረግ "በቤቴ መካከል" ከሚለው ሐረግ ጋር ትይዩ ነው፣ እሱም ሌለኛው ምክንያት የሆነ፣ መዝሙሩ በንጉሥ የተደረሰ ለመሆኑ።

**101፥8** ይህ ቁጥር የፍጻሜ ዘመን ቅኝት ያለው ይመስላል።

1. በየማለዳው (ማለትም፣ የብርሃን መምጣት፤ ወይም እንዲያው ንጉሡ አደባባይ የሚገኝበት፣ 2 ሳሙ. 15፡2)
2. ምድር (ማለትም፣ በርካታ ታሳቢ ፍችዎች ይኖሩታል፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር)
3. የእግዚአብሔር ከተማ (ራዕይ 21-22 ተመልከት፣ እዚያም ለእግዚአብሔር ሕዝቦች ሁሉ ምናባዊ ምስያ የሆነበት፣ ማለትም፣ "ቅድስቲቱ ከተማ፣ አዲሲቷ ኢየሩሳሌም")
4. አጠፋለሁ... ዓመጻ የሚያደርጉትን ሁሉ (ማቴ. 25:31-46፤ ራዕ. 20:11-15፤ 21:8፣27)

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ ንጉሣዊ መዝሙር ነውን? ለምን ወይስ ለምን አይደለም?
2. መዝ. 101፥1 የሚገልጸው ያህዌን ነው ወይስ ንጉሡን?
3. መዝ. 101፡2ለ ለመተርጎም ለምን አስቸጋሪ ሆነ?
14. መዝ. 101፡3 የሚያመለክተው ጣዖት አምላኪነትን (አመንዝራነትን) ነውን?
15. መዝ. 101፥8 ፍጻሜአዊ ነው ወይስ ሐሳባዊ?

# መዝሙር 102
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የተቸገረ ሰው ጸሎት፣ ለራሱ እና ለጽዮን ምሕረት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የተቸገረ ሰው ጸሎት፣ በዛለ ጊዜ ኀዘኑን በጌታ ፊት ሲያፈስስ | የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ፍቅር | በሕመም ጊዜ የፈውስ ጸሎት | የተቸገረ ወጣት ጸሎት | በክፉ ጊዜ ጸሎት |
| 102:1-7 | 102:1-2 | 102:1-2 | 102:1-2 | 102:1-2 |
| 102:8-11 | 102:3-7 | 102:3-11 | 102:3-8 | 102:3-5 |
| 102:12-17 | 102:8-11 | 102:12-17 | 102:9-11 | 102:6-8 |
| 102:18-22 | 102:12-17 | 102:18-22 | 102:12-17 | 102:9-11 |
| 102:23-28 | 102:18-22 | 102:23-24 | 102:18-22 | 102:12-14 |
| | 102:23-28 | 102:25-28 | 102:23-28 | 102:15-17 |
| | | | | 102:18-22 |
| | | | | 102:23-24 |
| | | | | 102:25-27 |
| | | | | 102:28 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 102፡1-7**

**[1]አቤቱ፥ ጸሎቴን ስማኝ፥**
**ጩኸቴም ወደ አንተ ይድረስ።**
**[2]በመከራዬ ቀን ፊትህን ከኔ አትመልስ**
**ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል**
**በጠራሁህ ቀን ፈጥነህ ስማኝ።**
**[3]ዘመኔ እንደ ጢስ አልቃለችና፥**
**አጥንቶቼም እንደ መቃጠያ ተቃጥለዋልና።**
**[4]እህል መብላት ተረስቶኛልና**
**ተቀሥፍሁ ልቤም እንደ ሣር ደረቀ።**
**[5]ከጩኸቴ ድምፅ የተነሣ**

**አጥንቶቼ ከሥጋዬ ጋር ተጣበቁ።**
**6እንደ ምድረ በዳ እርኩም መሰልሁ**
**በፈረሰ ቤት እንዳለ እንደ ጉጉት ሆንሁ።**
**7ተጋሁ፥ በሰገነትም እንደሚኖር ብቸኛ ድንቢጥ ሆንሁ።**

**102፡1-7** ይህ አንጓ የመዝሙረኛውን ሁኔታ ይገልጻል (ማለትም፣ "የመከራዬ ቀን፣" መዝ. 102:2፤23-26)።

1. ያህዌ ፊቱን እንደከለለ ተሰምቶታል (ማለትም፣ ምንም የእርሱ መገኘት አይሰማውም)
2. ዘመኑ እንደ ጢስ አለቀ፣ መዝ. 102፡3
3. አጥንቶቹ ተቃጥለዋል፣ መዝ. 102፡3
4. ልቡ ተመትቷል፣ መዝ.102፡4
5. እህል መብላት ተረስቶታል፣ ከጩኸቱ የተነሣ፣ 102፡4ለ-5ሀ
6. አጥንቱ ከሥጋው ጋር ተጣብቋል፣ መዝ. 102፡5ለ
7. በምድረ-በዳ እንዳለ ወፍ መስሏል፣ መዝ. 102፡6፤7ለ
8. መተኛት አልቻለም፣ መዝ. 102፡7ሀ

ሊሆን የሚችለው አካላዊ ሕመም የሚመስለው በርግጥ፣ ግለሰቡ በስደት እንዳለና በቤተ-መቅደሱ መጥፋት ነው (መዝ. 102:14፤18-22፤23-28)።

**102፡1-2** መዝሙሩ የሚጀምረው በተለጣጣቂ የጸሎት ጥያቄዎች ነው።

1. ጸሎቴን ስማ – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 17:6፤ 39:12፤ 54:2፤ 55:1፤ 61:1፤ 64:1፤ 143:1
2. የዕርዳታ ጩኸቴ ወደ ፊትህ ትድረስ – ቢዲቢ 9፣ ኬቢ 112፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. ፊትህን ከእኔ አትሰውር – ቢዲቢ 711፣ ኬቢ 771፣ *ሂፊል* ተጽዕኗዊ፣ መዝ. 27:9፤ 69:17፤ 143:7
4. ጆሮህን ወደ እኔ አዘንብል – ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 17:6፤ 31:2፤ 71:2፤ 86:1፤ 88:2
5. ፍጠን – ቢዲቢ 554፣ ኬቢ 553፣ *ፒል ተተኳሪ* ("ፈጠን በል፣" አኢመቅ ተመልከት፣ አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች የሚተረጉሙት እንደ ተውሳከ ግሥ ነው [ቢዲቢ 555])
6. መልስልኝ – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ *ቃል ተተኳሪ*

**102:2 "ፊትህን"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው ለያህዌ አካላዊ መገኘት (መዝ. 10:11፤ 13:1፤ 27:9፤ 30:7፤ 44:24፤ 51:9፤ 69:17፤ 80:3፤7፤19፤ 88:14፤ 143:7)።

▣ **"ቀን"** ይህ ምስያ (ቢዲቢ 398) ሦስት ጊዜ ተደግሟል።

1. በመከራዬ ቀን፣ መዝ. 102:2ሀ
2. በጠራሁህ ቀን፣ መዝ. 102:2c
3. ቀኖቼ፣ መዝ. 102:3ሀ
4. ቀኑን ሁሉ፣ መዝ. 102:8ሀ
5. ቀኖቼ፣ መዝ. 102፡11

ልዩ ርዕስ፡ ቀን (*ዮም*)

▣ **"ጆሮህን"** ይህ ሰዋዊ ምናባዊ ምስያ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሲገለጽ።

**102፡6 "እርኩም... ጉጉት"** በብኪ ዘወትር፣ ወፎችና የዱር እንስሳት የተተዉ ስፍራዎችን ለመግለጽ ብቻ አይደለም የሚጠቀሱት፣ ነገር ግን የአጋንንትን መገኘት እንጂ (ማለትም፣ ኢሳ. 13:19-22፤ 34:11-15፤ ሶፎ. 2:14)። እዚህጋ አትኩሮቱ ከመተው ወይም ከብቸኝነት ጋር በተያያዘ ነው።

ደግሞም ወፎቹ ከሌዋውያን አኳያ ንጹሕ አለመሆናቸውን ተመልከት (ሌዋ. 11፡13-19)፣ ይህም ያለመቀበልን ስሜት ማሳያ ሌላው መንገድ!

## መዝሙር ፡ 102፡8-11

**8ጠላቶቼ ሁልጊዜ ይሰድቡኛል፥**
**የሚያሳድዱኝም ተማማሉብኝ።**
**9አመድን እንደ እህል ቅሜአለሁና፥**
**መጠጤንም ከእንባዬ ጋር ቀላቅያለሁና፥**
**10ከቍጣህና ከመዓትህም የተነሣ**
**አንሥተኸኛልና፥ ጥለኸኛልና።**
**11ዘመኖቼ እንደ ጥላ አዘንብለዋል**
**እኔም እንደ ሣር ደርቄአለሁ።**

**102፡8-11** ይህ አንጓ ይቀጥላል፣ የተጎዳውን መዝሙረኛ ገለጻ።

1. የእርሱ ጠላቶች (ወራሪዎች ሊሆኑ ይችላሉ) ያለማቋረጥ ይሳለቁበታል፣ መዝ. 102፡8
2. የእርሱ ጠላቶች ያሾፉበታል
3. የእርሱ ጠላቶች ስሙን ርግማን አድርገውታል (ኢሳ. 65:15፤ ኤር. 29:22)

4-5. አመድን በልቷል እንባንም ጠጥቷል (እነዚህ የኀዘን ምልክቶች ናቸው፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የኀዘን ሥርዓቶች፣ መዝ. 42:3፤ 80:5)

6. ዘመኖቹ እንደ ጥላ አዘንብለዋል (ማለትም፣ መከራው የረጅም ጊዜ ነው)

7. እንደ ሣር ደርቋል (ዘፍ. 6:3፤ ኢዮብ 10:4፤ 14:1-2፤ መዝ. 78:39፤ 90:5-6፤ 102:4፤ 103:15-18፤ ኢሳ. 40:6፤ 1ጴጥ. 1:24-25)

ሥነ-መለኮታዊው ጉዳይ ለምን መከራ እንደሚቀበል ነው። መዝሙር 102፡10 የሚገልጠው መለኮታዊ ፍርድ እንዳገኘው ነው (መዝሙር 38)። አንዱ ሊደነቅ ይችላል እርሱ የሕዝብ ተምሳሌት ወይም ተወካይ ለመሆኑ (መዝ. 102:12-17፣18-22)።

**መዝሙር ፡ 102፡12-17**

**[12]አንተ ግን፥ አቤቱ፥ ለዘላለም ትኖራለህ፥**
**መታሰቢያህም ለልጅ ልጅ ነው።**
**[13]አንተ ተነሥ ጽዮንንም ይቅር በላት፥**
**የምሕረትዋ ጊዜ ነውና፥**
**ዘመንዋም ደርሶአልና**
**[14]ባሪያዎችህም ድንጋዮችዋን ወድደዋልና፥**
**ለመሬትዋም አዝነዋልና።**
**[15]አቤቱ፥ አሕዛብ ስምህን፥**
**ነገሥታትም ሁሉ ክብርህን ይፈራሉ**
**[16]እግዚአብሔር ጽዮንን ይሠራታልና፥**
**በክብሩም ይገለጣልና።**
**[17]ወደ ችግረኞች ጸሎት ተመለከተ፥**
**ልመናቸውንም አልናቀም።**

**102፡12-17** ይህ አንጓ ብሔራዊ አጽንዖት አለው። ያህዌ ለእስራኤል ዓለም አቀፋዊ ዓላማ አለው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

መዝሙረኛው ስለ ያህዌ የሚያስረግጣቸውን ተገሮች ተገንዘብ።

1. እሱ በዙፋኑ ለዘላለም ይቀመጣል (መዝ. 9:7፤ 10:16፤ 29:10፤ ሰቆ. 5:19)
2. ስሙ ("መታሰቢያ፣" ቢዲቢ 271፣ መዝ. 30:4፤ 97:12) ለትውልደ ትውልድ ነው (ዘጸ. 3:15፤ መዝ. 135:13)
3. በኪዳን ሕዝቡ ላይ በጸጋው ይሠራል
4. ጽዮንን ይሠራታል
5. እሱም ይከሰታል (ማለትም፣ ለጽዮን) በግርማው
6. የተቸገሩትን ጸሎት ይሰማል (ቢዲቢ 792፣ እዚህጋ ብቻ እና ኤር. 17፡6 ላይ ነው የሚከሰተው፣ እሱም ለዛፍ/ለቁጥቋጦ ጥቅም ላይ የዋለ፤ ሥሩ የመጣው "እርቃኑን ማስቀረት" ከሚለው ግሥ ነው)

መዝሙረኛው ያህዌን ይጠይቃል፣ ከእስራኤል ጎን ሆኖ እንዲሠራ፣ ለታላቁ ዓላማው!

**102፡13 "አንተ ተነሥ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086) ሰፊ የፍች መስክ አለው። እሱም የሚጠቅሰው

1. ያህዌ ሊሠራ ከዙፋኑ ሊነሣ (መዝ. 119:126)
2. ያህዌ ከእንቅልፉ ሲነቃ (ከድርጊት ለመታቀቡ ዘይቤ)
3. የያህዌ በንቃት መንቀሳቀስ፣ ከተወሰነ የሆን ብሎ ከሥራ መታቀብ በኋላ

▣ **"ዘመንዋም ደርሷልና"** ስሙ (ቢዲቢ 417) "በተቀጠረው ሰዓት" የሚል ፍች አለው (መዝ. 75፡2፤ ዳን. 8፡19)። ጽንሰ-ሐሳቡ፣ ማለትም፣ ያህዌ ጊዜን፣ ስፍራን፣ ታሪክን መቆጣጠሩ ለአንዱ እውነተኛው አምላክ ባሕርይ ማዕከላዊነት ነው (መክብብ 3)።

**102፡14-17** እነዚህ ቁጥሮች የመቅደሱን መፍረስ ያመለክታሉ።

1. አሕዛብ (ማለትም፣ ይሄንን ያደረጉ) ይፈራሉ፣ መዝ. 102፡15
2. ያህዌ ጽዮንን ይሠራታል፣ ክብሩንም ያሳያታል፣ መዝ. 102፡16
3. የችግረኛ ጸሎት (ማለትም፣ በስደት ላይ ያለው የእግዚአብሔር ሕዝብ) ይሰማል
4. መዝ. 102፡18-22 ተመልከት

**102፡14 "ባሪያዎችህም ድንጋዮችዋን ወድደዋልና፥"** ይህ ሐረግ የሚያስታውሰኝ ጥልቅ የሆነውን ስሜታዊ መተሳሰር ነው፣ ዘመናዊው ይሁዲነት ያለውን ለኢየሩሳሌም ግንብ ብርቱ ጩኸት (ማለትም፣ የሰሎሞን መቅደስ የመሠረት ድንጋዮች)። ይሁዲነት (ማለትም፣ የሙሴ ሕግ) ከልዩ የማምለኪያ ስፍራ ጋር ይያያዛል (ማለትም፣ የማደሪያው ድንኳን፣ ኋላም የኢየሩሳሌም ቤተ-መቅደስ)።

▣ **"ለመሬትዋም"** ይህ ስም (ቢዲቢ 779) ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለተደመሰሱ ከተሞች ፍርስራሽ ነው (1 ነገ. 20:10፤ ነህ. 4:2፣10፤ ሕዝ. 26:4፣12)።

**መዝሙር ፡ 102፡18-22**

**[18]ይህ ለሚመጣ ትውልድ ይጻፍ፥**
**የሚፈጠርም ሕዝብ ለእግዚአብሔር እልል ይላል**

**[19]እግዚአብሔር ከመቅደሱ ከፍታ ሆኖ ተመልክቶአልና፥**
**ከሰማይ ሆኖ ምድርን አይቶአልና**
**[20]የእስረኞችን ጩኸት ይሰማ ዘንድ፥**
**ሊገደሉ የተፈረደባቸውን ያድን ዘንድ**
**[21]የእግዚአብሔርን ስም በጽዮን**
**ምስጋናውንም በኢየሩሳሌም ይናገሩ ዘንድ**
**[22]አሕዛብ በአንድነት በተሰበሰቡ ጊዜ**
**መንግሥታትም ለእግዚአብሔር ይገዙ ዘንድ።**

**102፡18-22** ይህ አንጓ ያህዌ የኪዳን ሕዝቡን ወደ ይሁዳ እና መቅደሷ እንደሚመልስ ስለ ሰጠው ተስፋ ነው።
ዕብራውያን 1 ከመዝ. 102፡25-27 ጠቅሷል፣ ከኢየሱስ ጋር በተያያዘ። በዚህ መልኩ ምዝ. 102፡28 ከአዲሱ የእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ይዛመዳል (ማለትም፣ አማኝ አይሁድ እና አሕዛብ፣ ሮሜ. 2:28-29፤ 9:6፤ ገላ. 3:7-9፣13-14፣29፤ 6:15-16)!

**102፡19** ያህዌ በምድር ላይ ምን እንደሚሆን ያውቃል (ኢዮብ 28:24፤ መዝ. 14:2፤ 33:13-14፤ 53:3፤ 80:14፤ ሰቆ. 3:50፤ 5:1፤ መዝ. 33:13-17 ያለውን ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት)። "ምድር" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 75) በርካታ ፍችዎች ሊኖሩት ይችላል፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር።

▣ **"ከመቅደሱ ከፍታ ላይ … ከሰማይ"** እነዚህ ትይዩ ናቸው። የመጀመሪያው በሞሪያ ተራራ ላይ ያለውን መቅደስ የሚያመለክት ይሆናል፣ ነገር ግን ሁለቱም ግምት ውስጥ ተደርገው ሲወሰዱ፣ እሱ የሚያመለክተው የያህዌን መኖሪያ ስፍራ ነው፣ ከምድር ከባቢ አየር በላይ።

ልዩ ርዕስ፡ ሰማይ

ልዩ ርዕስ፡ ሰማይ እና ሦስተኛው ሰማይ

**102፡20** እነዚህ ምስያዎች የሚያመለክቱት የተጋዙትን ይሁዳውያንን ነው (እና እስራኤላውያንንም ሊሆን ይችላል)።

**102፡22** ይህ፣ በመጽሐፍ IV ላይ እንዳሉት በርካታ መዝሙራት ሁለንተናዊ አጽንዖት አላቸው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)። ሐረጉ፣ "መንግሥታትም ለእግዚአብሔር ይገዙ ዘንድ፣" የሚያስታውሰኝ ራዕ. 5፡9-14 እና 11፡15ን ነው።

## መዝሙር ፡ 102፡23-28

**[23]በኃይሉ ጎዳና መለሰለት።**
**የዘመኔን አነስተኛነት ንገረኝ።**
**[24]በዘመኔ እኩሌታ አትውሰደኝ**
**ዓመቶችህ ለልጅ ልጅ ናቸው።**
**[25]አቤቱ፥ አንተ ከጥንት ምድርን መሠረትህ፥**
**ሰማያትም የእጅህ ሥራ ናቸው።**
**[26]እነርሱ ይጠፋሉ፥ አንተ ግን ትኖራለህ**
**ሁላቸው እንደ ልብስ ያረጃሉ፥**
**እንደ መጐናጸፊያም ትለውጣቸዋለህ፥ ይለወጡማል**
**[27]አንተ ግን ያው አንተ ነህ፥**
**ዓመቶችህም ከቶ አያልቁም።**
**[28]የባሪያዎችህም ልጆች ይኖራሉ፥**
**ዘራቸውም ለዘላለም ትጸናለች።**

**102፡23-28** ይህ አንጓ፣ እንደ ሁለቱ ፊተኞች፣ ግለሰባዊ ምስያን በብሔራዊ መልኩ ይጠቀማል። እሱም የያህዌን የፍጥረት ድርጊት ያስረግጣል (መዝ. 102:26)፤ እሱ ዘላለማዊ ነው (102:27)! የእርሱ ሕዝቦች ጥፋት በተሞላበት ሁኔታ አልፈዋል (ሽንፈት፣ ጥፋት፣ ስደት)፣ ነገር ግን ይመልሳቸዋል (102፡28 ምክንያቱም "ሰማይ እና ምድር" የእጆቹ ሥራ እንደሆኑ (መዝ. 8:6፤ 19:1፤ ኢሳ. 45:12፤ 48:13)፣ እንዲሁ ደግሞ፣ የኪዳኑ ሕዝቦች ናቸው (መዝ. 138:8፤ 143:5፤ ኢሳ. 45:11፤ 60:2፤ 64:8፤ ሶርያ እንኳ ቢሆን፣ ኢሳ. 19:25)።

**102:23-24** LXX እነዚህን ቁጥሮች የሚተረጉመው ያህዌ መዝሙረኛውን እንደተናገረው ነው። የአኪ ዕብራውያን መጽሐፍ 1:10-12 መዝ. 102:25-27ን ጠቅሷል፣ ኢየሱስን እንደሚያመለክት። ሴምቲ ተመሳሳይ የዕብራይስጥ ተናባቢዎችን በተለየ መንገድ ይተረጉማቸዋል (ቲንዳሌ የብኪ (ሐተታ) ኮሜንተሪ፣ ቅጽ 16፣ መዝሙር 73-150፣ ገጽ. 395-396)።

**102፡23 "ብርታት"** ቃሉ (ቢዲቢ 470) ጥቅም ላይ የዋለው ብሔራዊ ጥንካሬ በያህዌ ፍርድ መጎዳቱን ነው (ሌዋ. 26:20፤ ሰቆ. 1:6፣14፤ አሞጽ 2:14)።

**102:25-27** እነዚህ ቁጥሮች ከLXX የሆኑት ዕብ. 1:10-11 ላይ ተጠቅሰዋል፣ እዚያም ለኢየሱስ ጥቅም ላይ ውለው (ዕብ. 13:8)።

**102:27 "አንተ ግን ያው አንተ ነህ"** ያህዌ አይለወጥም፣ ዓላማውም ቢሆን (መዝ. 33:11፤ ሚል. 3:6፤ ያዕቆብ 1:17)። መዝሙር 102:27 አስገራሚ ተቃርኖ ነው ለ 102:26። ሰማይና ምድር እንኳ ያልፋሉ (ኢሳ. 34:4፤ 51:6፤ ማቴ. 5:18፤ 24:35፤ ማርቆስ 13:31፤ ሉቃስ 21:33፤ 2 ጴጥ. 3:10፤ ራዕ. 20:11)፣ ያህዌ ሳይሆን!

ለእግዚአብሔር ያለመለወጥ መልካም አጭር ማብራሪያ ሚላርድ ኢሪክሰን፣ *የክርስቲያን ሥነ-መለኮት*፣ 2ኛ ዕትም ገጽ 304-308 ተመልከት።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ስለ ግለሰብ ነው ወይስ ስለ እስራኤል ሕዝብ?
2. የመዝ. 102፡6 ምናባዊ ምስያ አብራራ።
3. መዝ. 102፡14 አንድምታው የመቅደሱን መፍረስ ለመጥቀስ ነውን?
4. የመዝ. 102፡15፤22 ሁለንተናዊ አጽንዖት የሚያመለክተው ከስደት መመለስን ነው ወይስ የፍጻሜ ዘመንን መቼት?
5. ሰማይና ምድር ቋሚ ናቸው ወይስ ጊዜያዊ?
6. መዝ. 102፡28 እንዴት ይዛመዳል ከ
   ሀ. ዘፍ. 12፡1-3 ጋር
   ለ. ሮሜ. 2፡28-29 ጋር

# መዝሙር 103
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ምስጋና ለእግዚአብሔር ምሕረት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር | ምስጋና ለእግዚአብሔር ምሕረት | ምስጋና ከሕመም በዳኑ ጊዜ | የእግዚአብሔር ፍቅር | እግዚአብሔር ፍቅር ነው |
| 103:1-5 | 103:1-5 | 103:1-5 | 103:1-5 | 103:1-2 |
| | | | | 103:3-5 |
| 103:6-14 | 103:6-10 | 103:6-14 | 103:6-14 | 103:6-7 |
| | | | | 103:8-10 |
| | 103:11-14 | | | 103:11-12 |
| | | | | 103:13-14 |
| 103:15-18 | 103:15-18 | 103:15-18 | 103:15-18 | 103:15-16 |
| | | | | 103:17-18 |
| 103:19-22 | 103:19 | 103:19-22 | 103:19-22 | 103:19-20 |
| | 103:20-22 | | | 103:21-22 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ አንደኛው ከፍ ያለ የምስጋና ምልክት ካለባቸው መዝሙሮች አንደኛው ነው። እሱም የመዝሙር 104 ተጓዳኝ ነው። መዝሙር 103 የሚያተኩረው እግዚአብሔር ምሕረትን እንደ ተሞላ ተቤዢ ነው (ያህዌ፣ መዝ. 103፡1፣6፣8፣13፣17፣19፣20፣21፣22 [ሁለቴ])፣ መዝሙር 104 ደግሞ የሚያተኩረው በእግዚአብሔር የፈጠራ ኃይል ላይ ነው (ኤሎሂም፣ መዝ. 104፡1፣33)።

ለ. ይህ መዝሙር የሚያመራው (1) የግል ልምምድ (2) ወደ ጋራ አምልኮ (3) ሁሉን አቀፍ አምልኮ ነው።

ሐ. አጭር የፍሬ-ሐሳብ ዝርዝር
1. ምስጋና ለእግዚአብሔር፣ ለግለሰቦች ላለው ፍቅር፣ መዝ. 103:1-5
2. ምስጋና ለእግዚአብሔር፣ ለእስራኤል ላለው ፍቅር፣ መዝ. 103:6-14
3. ምስጋና ለእግዚአብሔር፣ ወሰን ለሌለው ፍቅሩ፣ ለውስኑ ሰው፣ መዝ. 103:15-18
4. ሁሉም እግዚአብሔርን ያመስግን መዝ. 103:19-22

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 103፡1-5**

**[1]ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥**
**አጥንቶቼም ሁሉ፥ የተቀደሰ ስሙን።**

[2]ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ፥
 ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ
[3]ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል፥
 ደዌሽንም ሁሉ የሚፈውስ፥
[4]ሕይወትሽን ከጥፋት የሚያድናት፥
 በምሕረቱና በቸርነቱ የሚከልልሽ፥
[5]ምኞትሽን ከበረከቱ የሚያጠግባት፥
 ጕልማስነትሽን እንደ ንስር ያድሳል።

**103:1-2፣20-22 "እግዚአብሔርን ባርኪ"** አንዱ የዚህን መዝሙር የመጀመሪያውንና የመጨረሻውን ስንኞች እና መዝ. 104:1፣35 ሲያስተያይ፣ አንድነት እንደሚበጥሩ ግልጽ ነው (ስድስት ፔይል ተተኳሪዎች)።

▣ **"ባርኪ"** ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 138፣ ኬ.ቢ. 159) ከሁለት አንደኛው ሥር ነው፣ ለበረከት ጥቅም ላይ ከዋሉት።

1. ገሠአ (ቢ.ዲ.ቢ. 80) 45 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እናም ማቴ. 5:3-10 ካለው "የተባረከ" ጋር ትይዩነት አለው (ማለትም፣ የላቀ ደስታ)። እሱም የመባረክን አቋም ይገልጻል (መዝ. 1:1፤ 2:12፤ 32:1፣2፤ 33:12፤ 34:8፤ 40:4፤ ወዘተ.)።
2. ገገ፱. (ቢ.ዲ.ቢ. 138) እዚህጋ ጥቅም ላይ ውሏል (መዝ. 103:1፣2፣20፣21፣21፤ 104:1፣35) እና ከ325 በላይ ብኪ. ላይ።
 እሱም ጥቅም ላይ የዋለው
 ሀ. ለያህዌ በረከት፣ ለመነሻው ፍጥረት – ዘፍ. 1:22፣ 28
 ለ. ያህዌ አባቶችን ባርኳል – ዘፍ. 12:1፤ 18:18፤ 22:17-18፤ 26:4፤ 28:14
 ሐ. የኪዳን ታዛዥነት ርግማንና በረከት — ዘዳግም 27-28 (ደግሞ ሌዋውያን 26ን እይ)
 መሠረታዊው ሥር ሁለት ፍችዎች አሉት (የተዛመዱ የሚሆኑ)
 ሀ. መንበርከክ
 ለ. መባረክ

**103:1 "ነፍስ"** *ኔፌሽ* (ቢ.ዲ.ቢ. 659፣ ኬ.ቢ. 711-713) የዕብራይስጥ ቃል "የሕይወት ኃይል" ነው። እሱም ለሁለቱም ለሰው ልጅ (ዘፍ. 2:7) እና ለእንስሳት ጥቅም ላይ ይውላል (ዘፍ. 1:24፤ 2:19)። እዚህጋ ከቀጣዩ ሐረግ ጋር ትይዩ ነው፣ "በእኔ ውስጥ ያለው ሁሉ፣" ይኸውም ደራሲው እግዘኢአብሐሔርን በሁለንተናው ለማመስገን ጥረት የሚያደርግበትን አጽንዖት ለመስጠት ነው። መዝ. 3:2 ላይ ያለውን ማስታወሻ፣ ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ላይ ተመልከት።

▣ **"ነፍሴ ሆይ"** ይህ ጽሑፋዊ መልክ ነው ደራሲው ለራሱ የሚናገርበት (መዝ. 42:5፣11፤ 43:5፤ 104:1፣35፤ 116:7)። እሱም የአንዱን የግል አስተሳሰብ ሂደት መንገድ የሚጠቅስ ነው።

▣ **"ቅዱስ ስሙን"** ቀሪው የመዝሙሩ ክፍል፣ በተለይም መዝ. 103:8-14 የእግዚአብሔርን ባሕርይ ይገልጻል። ይህ መዝሙር እውነተኛውን ስዕል እንድናገኝ ይረዳናል፣ የዘላለማዊውን፣ ፈጣሪ፣ የሚቤዥ አምላክ ልብና ሐሳብ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት።

**103:2 "ምስጋናውንም ሁሉ አትርሺ"** ብኪ. ላይ፣ ለእግዚአብሔር መርሳት ማለት እጅግ ጠቃሚ ነው፣ ምክንያቱም ስለ ይቅርታው ስለሚናገር። ነገር ግን ለሰው፣ መርሳት ማለት የእርሱን ምስጋና-ቢስነት ወይም ዓመጻ የሚናገር ነው። የተሻለ ትይዩ ምንባብ ስለ እግዚአብሔር አስደናቂ ምሕረት፣ በወደቀው ሰው ላይ የሚታየው ዘዳ. 4:9፣23፣31፤ 6:12፤ 8:11፣14፣19፤ 9:7፤ 25:19። እንዲያው ተቀምጦ ማንጸባረቅ ነው፣ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ፣ ለእኛ ምን እንዳደረገልን፣ ለልብ ደስታን ወደ እውነተኛ አማኝ ያመጣል።

**103:3 "ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል"** ቃሉ (ቢ.ዲ.ቢ. 699፣ ኬ.ቢ. 757) ለ "ይቅርታ" በዕብራይስጥ ጥቅም ላይ የዋለው፣ ለእግዚአብሔር ይቅርታ ብቻ ነው። መዝሙር 103:11-13 ሦስት ዘይቤዎችን ይጨምራል፣ የእግዚአብሔርን ይቅርታ በምስል-ከሳች ቃላት የሚገልጹ።

▣ ተለጣጣቂዎቹን አንቀጾች (ግሥ)፣ እነርሱም ያህዌ ለምን እንደሚመሰገን የሚገልጹትን ተገንዘብ (ማለትም፣ ጠቀሜታዎችን ይሰጣል)።

1. ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር የሚል – ቢ.ዲ.ቢ. 699፣ ኬ.ቢ. 757፣ *ቃል*
2. ደዌሽን ሁሉ የሚፈውስ – ቢ.ዲ.ቢ. 950፣ ኬ.ቢ. 1272፣ *ቃል*
3. ሕይወትሽን ከጉድጓድ የሚቤዥ – ቢ.ዲ.ቢ. 145፣ ኬ.ቢ. 169፣ *ቃል*
4. በምሕረቱና በቸርነቱ የሚከልልሽ – ቢ.ዲ.ቢ. 742፣ ኬ.ቢ. 815፣ *ፒል*
5. ዘመኖችሽን ከመልካም ነገር ያጠግባል – ቢ.ዲ.ቢ. 959፣ ኬ.ቢ. 1302፣ *ሂፊል*

እነዚህ አምስት ተለጣጣቂ አንቀጾች (ግሥ) በምድር ላይ ያለውን ሕይወት እና ወደፊት በሰማይ የሚኖረውን ሕይወት ይሸፍናሉ።

▣ **"ደዌሽን ሁሉ የሚፈውስ"** የዕብራይስጡ ስም፣ "ደዌ" (ቢ.ዲ.ቢ. 316)፣ እና ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 317 I) ዘዳ. 29:21 ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል፣ በርግማን መልኩ፣ እስራኤል ለኪዳኑ አልታዘዝም ስላለ። ከዚህ አጠቃቀም የተነሣ፣ እና ከበርካታ የብኪ. ምንባቦች፣ እነርሱም ከኃጢአት ስለመፈወስ የሚገልጹ (መዝ. 41:4፤ ኢሳ. 1:6፤ 6:10፤ 53:5)፣ የዚህ ቁጥር አጽንዖት ከሥጋዊ ፈውስ ነው ብሎ ለመውሰድ ያጠራጥራል፣ ምንም እንኳ እሱ በርግጥ (ዘጸ. 15:26፤ ዘዳ. 32:29፤ መዝ. 147:3ን ቢያካትትም)። አይሁድ የሚገነዘቡት ኃጢአትና ሕመም እንደሚዛመዱ ነው (ያዕቆብ 5:13-18)። እዚህጋ፣ እሱ ትይዩ ነው "ኃጢአትሽን ሁሉ ይቅር" ከሚለው ጋር።

ልዩ ርዕስ፡ ፈውስ

**103፡4 "ሕይወትሽን የሚቤዥ"** "ይቤዣል" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 145፣ ኬቢ 169፣ *ቃል የድርጊት አንቀጽ*) "የዘመድ ተቤዢ" ከሚለው ጋር ተመሳሳይ ነው ወይም ጎል (ቢዲቢ 145፣ *ቃል የድርጊት አንቀጽ*፣ ኢዮብ 19:25 እና ደግሞ ከሩት 4 ጋር ተመሳሳይ ሥር)። እዚህጋ፣ እግዚአብሔር በቅርብ ቤተሰባዊ ቃላት ተገልጿል፣ መዝ. 103፡13 ላይ እንዳለው።

▣ **"ከጉድጓድ"** ይህ ከሥጋዊ ጥፋት አኳያ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፣ ነገር ግን ሲኦል ከሚለው ቃል መዝ. 16፡10 ካለው የትይዩነት ዝምድና የተነሣ፣ እሱ ከደራሲው የከሞት በኋላ ተስፋ ጋር የሚዛመድ ይመስላል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው?)። አንዳንድ ደራስያን ይልቁንም ከመዝ. 103፡4ለ እና 5 ጋር ይሄንን ዐውደ-ጽሑፍ ያያይዙታል።

▣ **"በምሕረቱ የሚከልልሽ"** *ግሥ* (ቢዲቢ 742፣ ኬቢ 815) ሊል የሚችለው

1. አክሊል – LXX እና አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች
2. መክበብ – ጀፒኤስኦኤ፣ ኒዶቲ፣ ቅጽ. 3፣ ገጽ 384

ሁለቱም ስሜት ይሰጣሉ፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ።

▣ **"ርኅራኄ"** *ቃሉ* (ቢዲቢ 933) አዘውትሮ ለያህዌ ነው ጥቅም ላይ የሚውለው (ዘጸ. 33:19፤ ዘዳ. 13:17፤ 30:3፤ 2 ነገ. 13:23፤ ኢሳ. 14:1፤ 30:18፤ 49:10፣13፤ 54:8፣10፤ 55:7፤ 60:10)። እሱም መዝ. 102:14 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ የስደትን ስሜቶች ለመግለጽ፣ ስለ ፈረሰው መቅደስ (ሰቆ. 3:22)።

▣ **"ዘመንሽን ከመልካም ነገር የሚያጠግብ"** ይህ እጅግ አስቸጋሪ ቁጥር ነው፣ ለመተርጎም፣ ምክንያቱም ከዕብራይስጡ ቃል "ዘመናት" ርግጠኛ ያለመሆን የተነሣ። እሱ በጥሬው የሚለው "ጌጣ ጌጥ" ነው (ቢዲቢ 725)። ኪንግ ጀምስ ትርጉም፣ "አፍ፣" ትክክል እንዳልሆነ ግልጽ ነው። አምቀ ትርጉም ከሴፕቱዋጂንት እና ቫልጌት ጋር ተጎዳኝተው፣ "መሻት" የሚል አላቸው፣ እሱም ከዋናው ቃል ተወራራሽ ፍቺ የሚመስል፣ በአንጻሩ አብዛኞቹ ዘመናዊ ትርጉሞች ጽሑፋዊ እርማትን ይወስዳሉ፣ የሕይወትን ወይም ቀዳሚ ሕይወትን ጽንሰ-ሐሳብ ለማምጣት (አእመቅ፣ የተመት፣ አእመቅ እና ጀፒኤስኦኤ)። ኤቢ (ሚካኤል ዳሆድ፣ ገጽ 26) እሱን የሚመለከተው ዘላለማዊነትን እንደሚጠቅስ ነው (ማለትም፣ ሕይወት ከእግዚአብሔር ጋር በሰማይ)። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ለ "ጌጣጌጥ" "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል፣ (መጠነኛ ጥርጣሬ)።

▣ **"ጕልማስነትሽን እንደ ንስር ያድሳል።"** "ንስር" የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ፣ አንዳንድ ተንታኞች ይሄንን ቁጥር በሁለት የተለያዩ መንገዶች እንዲመለከቱ አድርጓቸዋል።

1. በመሠረቱ የሚያመለክተው የንስርን ብርቱ ጥንካሬ ነው (ኢሳ. 40፡31)
2. የዓረብ ወፍ አፈ-ታሪካዊ ጠቃሽ፣ ከሞት በኋላ ተመልሳ ወደ ሕይወት የምትመጣ ወፍ (የተመቅ ትርጉም፤ ኢዮብ 29፡18 ሊሆን ይችላል)
3. ንስሮች ገላቸውን ያራግፋሉ አዲስ ላባ ለማግኘት (አእት መጽሐፍ ቅዱስ)

"ንስርን" የተረጎመው ቃል (ቢዲቢ 676) አሞራን ወይም ጥንብ-አንሣን ሊያመለክት ይችላል። በዚህ የያህዌ የምሕረትና የጸጋ ዐውደ-ጽሑፍ፣ "ንስር" የተሻለው አማራጭ ነው (ዘጸ. 19:4፤ ዘዳ. 32:11፤ ኢሳ. 40:31 ተመልከት)።

"ያድሳል" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 293፣ ኬቢ 293) ያልተለመደ ነው (1 ሳሙ. 11:14፤ 2 ዜና. 15:8፤ 24:4፣12፤ ኢዮብ 10:17፤ ኢሳ. 61:4፤ ሰቆ. 5:21)። እሱም ሦስት ጊዜ ብቻ መዝሙር ላይ ጥቅም ላይ ውሏል።

1. መዝ. 51:10 – የቀናውን መንፈስ በውስጤ አድስ (*ፒኤል ያልተጠናቀቀ*)
2. መዝ. 103:5 – እንደ ንስር ያድሳል (*ሂዝፔል ያልተጠናቀቀ*)
3. መዝ. 104:30 – የምድሩን ገጽታ ታድሳለህ (*ፒኤል ያልተጠናቀቀ*)

***መዝሙር* ፡ 103፡6-14**

**6 እግዚአብሔር ይቅርታ አድራጊ ነው**
**ለተበደሉ ሁሉ ይፈርዳል።**
**7 ለሙሴ መንገዱን አስታወቀ፥**
**ለእስራኤል ልጆችም አደራረጉን።**
**8 እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ ነው፥**
**ከቍጣ የራቀ ምሕረቱም የበዛ።**
**9 ሁልጊዜም አይቀሥፍም፥**
**ለዘላለምም አይቈጣም።**
**10 እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም፥**
**እንደ በደላችንም አልከፈለንም።**
**11 ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥**
**እንዲሁ እግዚአብሔር ምሕረቱን በሚፈሩት ላይ አጠነከረ።**
**12 ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፥**
**እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ።**
**13 አባት ለልጆቹ እንደሚራራ**
**እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል**
**14 ፍጥረታችንን እርሱ ያውቃልና**
**አቤቱ፥ እኛ አፈር እንደ ሆንን አስብ።**

**103፡6፣7 "እግዚአብሔር ይቅርታ አድራጊ ነው"** "የጽድቅ ሥራ" የሚለው ቃል በብኪ ሁለት መንገዶችን ይጠቀማል።

1. የእግዚአብሔርን ቅድስና ለመግለጽ
2. የእግዚአብሔርን የማዳን ሥራ ለመግለጽ

እነዚህ ሁለት ቁጥሮች የሚሰጡን ገለጻ የዘጸአትን እና የምድረ-በዳ መንከራተትን ሁነቶች ይመስላል። ስለዚህ፣ ይህ ሥስትዮሽ ምስጋና ነው፣ ለእግዚአብሔር የጸጋ ድርጊት

1. ከግብፅ ማውጣት
2. ራሱን ለሙሴ መግለጽ
3. በምድረ-በዳ መንከራተት ጊዜ ሕዝቡን መታገሡ

◘ **"ለተበደሉ ሁሉ ይፈርዳል።"** እንደዚህ ዓይነቶቹን ጽሑፎች ለመተርጎም ሁለት መንገዶች አሉ።

1. እግዚአብሔር ለደካማ፣ ለደሀ፣ እና አቅም ለሌለው ይጠነቀቃል (ማለትም፣ ዘጸ. 22:22-24፤ ዘዳ. 10:17-19፤ መዝ. 68:5)።
2. ብኪ ብልጽግናን የሚመለከተው ከእግዚአብሔር ዘንድ ሞገስን እንደማግኘት አድርጎ እስከሆነ ድረስ፣ ዘወትር ሎጂካዊ ድምዳሜው ሌሎችን እንደተዋቸው ነው፣ ከኃጢአታቸው የተነሣ (ማለትም፣ ኢዮብ፣ መዝሙር 73)፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ተደጋጋሚ ፍቅር መመልከት ይቻላል፣ ለእነርሱ በተለመደው የማሳያ/የማጽኛ መንገድ፣ ፍቅሩና ክብካቤው ለሁሉም እንደሆነ!

**103:7 "ለሙሴ መንገዱን አስታወቀ፥"** ያህዌ ራሱን ለሙሴ ገልጧል፣ ዘጸአት 19-20፤ 33:13፤ መዝ. 99:7. ብኪ ተመስጧዊ፣ ዘላለማዊ መገለጥ ነው (ማቴ. 5:17-19)፣ ነገር ግን መታወስ ያለበት ኢየሱስ የመዳረሻው መገለጥ መሆኑ ነው (ማቴ. 5:21-48)። እሱ ብቸኛው ትክክለኛው የቅዱስ ቃሉ ተርጓሚ ነው። እሱ የቅዱስ ቃሉ ጌታ ነው! ሙሴያዊው መገለጥ በመቀደስ ላይ አሁንም ይሠራል፣ በማጽደቅ ላይ ግን አይደለም።

ልዩ ርዕስ፡ የጳውሎስ የሙሴ ሕግጋት አተያይ

ልዩ ርዕስ፡ ተመስጦ

ልዩ ርዕስ፡ መንፈሳዊ ማብራሪያ

◘ **"መንገዶቹ"** ይህ ከበርካቶቹ ቃላት አንዱ ነው፣ የያህዌን መገለጥ ለመግለጽ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር መገለጥ።

**103:8 "እግዚአብሔር መሐሪና ይቅር ባይ ነው፥ ከቍጣ የራቀ ምሕረቱም የበዛ።"** ይህ የመጀመሪያው ሐረግ ነው፣ ተለጣጣቂ ከሆኑ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ከሚገልጹ። እሱም የዘጸ. 34፡6፣7 ጠቃሽ ይመስላል። እነዚህ የእግዚአብሔር አስተዋጽዖዎች በተደጋጋሚ በቅዱስ ቃሉ ላይ በአጽንዖት ተገልጸዋል (ዘኍ. 14:18፤ ዘዳ. 4:31፤ ነህ. 9:17፤ መዝ. 86:15፤ 145:8፤ ኢዩኤል 2:13፤ ዮናስ 4:2)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት።

**103:9 "ሁልጊዜ አይቀሥፈንም"** አንዱ ይሄንን በእንግሊዝኛ ይሄንን ሲያነብ፣ እግዚአብሔር ዘወትር በወደቀው ሰው ላይ ትዕግሥት እንደሌለው ይመስላል፣ ነገር ግን በዕብራይስጦ ፈሊጥ ፍጹም ተቃራኒው ነው! እሱ ዘወትር ትዕግሥት አለው በልዩ ፍጡሩ ላይ (ዘፍ. 6:3፤ ኢሳ. 57:16)።

◘ "ማስጨነቅ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 936፣ ኬቢ 1224፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*) የሕግ ክሶችን የሚጠቅስ ቃል ነው (ኤር. 3፡5፣12)። የእግዚአብሔር ልብ ዘወትር ፍቃደኛ ነው፣ ወደ እኛ ለመመለስ፣ ወደ እርሱ ስንመለስ (ያዕቆብ 4፡8)!

**103:10 "እንደ ኃጢአታችን አላደረገብንም፥እንደ በደላችንም አልከፈለንም።"** ታማኝ ተከታዮች ከኃጢአታቸው ጋር በተያያዘ አይቀጡም አልያም በጥረታቸው መሠረት አይከፈሉም። ይህ ቁጥር በግልጽ የሚቀጥለው የመዝ. 103፡9ን አስተሳሰብ ነው፣ እስራኤልም የእርሱን እውነት በደንብ ያውቃል።

**103:11 "ሰማይ ከምድር ከፍ እንደሚል፥"** ይህ ከሦስቱ ዘይቤዎች የመጀመሪያው ነው፣ የእግዚአብሔርን ወሰን የሌለው ጸጋ ከሚገልጹት። ለ "ሰማይ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማይ እና ለዩ ርዕስ፡ ሰማይና ሦስተኛ ሰማይ። ኢሳ. 55፡9 ላይ ትይዩውን ተመልከት።

◘ **"የሚፈሩት"** ግሥ (ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ *ቃል የድርጊት አንቀጽ*) "አክብሮት"ን "ፍርሃት"ን ይገልጻል። ይህ ሐረግ ተደጋጋሚ መጠሪያ ነው፣ ለታማኝ ተከታዮች (መዝ. 15:4፤ 25:12፣14፤ 103:13፤ 118:4)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፍርሃት (ብኪ)፣

**103:12 "ምሥራቅ ከምዕራብ እንደሚርቅ፥"** የዕብራይስጥ ሥርወቃል "ምስራቅ" እና "ምዕራብ" የፀሐይን መውጣትና መግባት ያመለክታል። የሰማያት ከፍታ ከእግዚአብሔር ጸጋ ጋር ሊወዳደር እንደማይችል ሁሉ፣ እንዲሁ ከአድማስ እስከ አድማስ ያለው የምድር ስፋት ከእግዚአብሔር ጸጋ ጋር ሊወዳደር አይችልም። አንዱ ይሄንን ከኢሳ. 38፡17፤ 44፡22፤ እና ሚኪያስ 7፡19 ጋር ቢያነጻጽር ሙሉው የእግዚአብሔር ጸጋ ዘይቤአዊ አንድምታ እጅግ ይበረታል!

◘ **"እንዲሁ ኃጢአታችንን ከእኛ አራቀ።"** "አራቀ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 934፣ ኬቢ 1221) የሚገልጸው "ምንም ግንኙነት አለማድረግ ነው፣" ይኸውም የሚያሳየው የኃጢአትን ቅጣት እና ኩነኔ ሙሉ ለሙሉ መወገድ ነው፣ በቸሩ አምላክ።

ይህ የብኪ በጸጋ መጽደቅ ነው! እግዚአብሔር ይቅር ሲል (ከእርሱ ማንነት የተነሣ)፣ ይረሳዋል (ኢሳ. 1:18፤ 38:17፤ 43:25፤ 44:22፤ ሚኪያስ 7:19)! ያለፈዋችን ይቅር ተብሏል ተረስቷልም። እንግዲህ ወደፊት የጽድቅ ኑሮን መኖር አለብን። ብዙ አማኞች በእውቀት በሆነ መልኩ የእግዚአብሔርን ይቅርታ ሊያረጋግጡ ይችላሉ፣ ነገር ግን እግዚአብሔር እንደሚረሳ ፈጽሞ በሙሉት አይዙም!

መዝ. 103:12-13 ላይ ሁለት ቃላት በ ፊ የሚጀምሩ እንዳሉ ተገንዘብ፣ እነዚህም ሁለቴ ይከሰታሉ። ይህ ግልጽ የሆነ የድምጽ መቀያየር ነው (ልክ በሦስትዮሽ ג ድምጽ መዝ. 103:10 እና 11 ላይ እንዳለው።

**103:13 "አባት ለልጆቹ እንደሚራራ"** እዚህም ሌለኛው ቤተሰባዊ ዘይቤ ነው፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር ለመግለጽ (ዘጸ. 4:22፤ ዘዳ. 1:31፤ 8:5፤ መዝ. 27:10፤ ምሳ. 3:12፤ ኢሳ. 49:15፤ 63:16፤ 64:8፤ ኤር. 31:9፤ ሆሴ. 11:1፤ ሚል. 1:6)። ይህ ታሳቢ መነሻ የኢየሱስ ቃል ነው፣ እግዚአብሔርን እንደ አባት ለመግለጽ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አባት እና ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር አባትነት)።

ይህ ቁጥር በይሁዲነት ጥቅም ላይ ይውል ነበር፣ በስርየት ቀን (ሌዋውያን 16)። እሱም የሚጠቀሰው ከሁለቱ የመሥዋዕት ፍየሎች አንደኛው ወደ ገደል ሲገፋ (ማለትም፣ ኃጢአትን ከሰፈር ማስወገድ)።

▣ **"እንዲሁ እግዚአብሔር ለሚፈሩት ይራራል"** መታሰብ የሚኖርበት፣ ምንም እንኳ የእግዚአብሔር መነሻ ጸጋ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ቁልፍ ቢሆንም፣ ከሰው ልጆች ምላሽን ይጠይቃል፣ በመነሻውና በሂደት ላይ ባለው መንገድ (መዝ. 103፡17፣18 በሰው ልጅ በኩል ለሆነው ሦስትዮሽ ሁኔታዊ የአጽንዖት ገጽታ)።

"ፍርሃት" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ ቃል የድርጊት አንቀጽ) የሚያመለክተው እግዚአብሔርን የሚፈሩትን ነው፣ በእምነት እና ታማኝነት። ሙሉውን ማስታወሻ ተመልከት የ "ፍርሃት" አዎንታዊና አሉታዊ ገጽታዎች፣ መዝ. 15፡2-5። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፍርሃት (ብኪ.)።

**103:14 "ፍጥረታችንን እርሱ ያውቃልና"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል የትዜር *(yetzer)* ነው (ቢዲቢ 428)፣ ፍችውም "ሐሳብ (ውስጣዊ)።" እግዚአብሔር ሐሳባችንን ያውቃል፣ አሁንም ግን ይወደናል (ዘፍ. 6:5፤ 8:21)። አስገራሚ የሚሆነው፣ ባጠቃላይ ራቢዎች በመነሻ ኃጢአት አለማመናቸው ነው (ዘፍጥረት 3)፣ ነገር ግን በሁለቱ *yetzers (ሐሳቦች)* ንድፈ-ሐሳብ ተይዘዋል (ማለትም፣ መልካም ሐሳብና ክፉ ሐሳብ)። እነርሱ የሚሉት፣ እያንዳንዱ ሰው ጥቁር ውሻ እና ነጭ ውሻ በውስጡ አለው፣ እናም ደኅና አድርጎ የሚመግበው እሱ ትልቅና ጠንካራ ይሆናል። ይኸም ለሰዎች ኃላፊነት አጽንዖት የሚሰጥ ነው፣ እሱም በርግጥ ግማሽ እውነት የሆነ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምርጫ/ዕጣ ፈንታ/ እና የሥነ-መለኮታዊ ሚዛን አስፈላጊነት)።

አየተመቅ እና ጄፒኤስኦኤ ግሡን የሚመለከቱት፣ መዝ. 103:4ሀ ላይ ያለውን፣ የአዳምን ፍጥረት እንደሚመለከት ነው (ዘፍ. 2:7፤ 3:19) ወይም ሰዎችን ሁሉ (መዝ. 139:15)። አእቅ እና አኢመቅ የሚሉት እሱ የሚመለከተው ሰዎች ከምን እንደተሠሩ ነው (ማለትም፣ ሸክላ፣ አፈር)።

▣ **"አቤቱ፥ እኛ አፈር እንደ ሆንን አስብ።"** ይህ ዘይቤ የሚያመለክተው የመነሻውን ፍጥረት ነው (ዘፍ. 2:7፤ 3:19፤ ኢዮብ 34:15 መዝ. 104:29፤ መክ. 3:20፤ 12:7)። እሱም የሚናገረው ስለ ሰው ልጆች ደካማነት ነው (ኢዮብ 10:9፤ መዝ. 78:39)፣ ይኸውም ቀጣዩን ክፍል የሚያስተዋውቅ፣ መዝ. 103:15-18።

***መዝሙር ፡ 103፡15-18***

**[15]ሰውስ ዘመኑ እንደ ሣር ነው**
**እንደ ዱር አበባ እንዲሁ ያብባል**
**[16]ነፋስ በነፈሰበት ጊዜ ያልፋልና፥**
**ስፍራውንም ደግሞ አያውቀውምና።**
**[17]የእግዚአብሔር ምሕረት ግን ከዘላለም እስከ ዘላለም በሚፈሩት ላይ፥**
**ጽድቁም በልጅ ልጆች ላይ ነው**
**[18]ቃል ኪዳኑን በሚጠብቁ፥**
**ትእዛዙንም ያደርጉአት ዘንድ በሚያስቡ ላይ ነው።**

**103:15፣16 "ሰውስ ዘመኑ እንደ ሣር ነው"** ይህ አንጓ (መዝ. 103፡15-18) አጽንዖት የሚሰጠው ለእግዚአብሔር ዘላለማዊነት እና ለሰው ልጅ ረብ-የለሽ ውስንነት ነው። ይኸው ተመሳሳይ ዘይቤ ብኪ ላይ በርካታ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (ኢዮብ 14:1፣2፤ መዝ. 90:5፣6፤ ኢሳ. 40:6-8)፣ እና አኪ ላይ (1 ጴጥ. 1:24-25)።

**103፡17-18** እነዚህ ቁጥሮች ሦስትዮሽ ተለጣጣቂዎችን ይዘዋል፣ እነርሱም የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር የመነሻ ፍቅር ምላሽ መስጠት እንዳለበት የሚገልጹ (ማለትም፣ የሰው ነጻ ፍቃድ)።

1. መዝ. 103:17፣ የሚፈሩት እነርሱ
2. መዝ. 103:18፣ ኪዳኑን የሚጠብቁ
3. መዝ. 103:18፣ ትእዛዙንም ያደርጓት ዘንድ የሚያስቡ

**103፡17 "የእግዚአብሔር ምሕረት"** ይህ የእርሱን የኪዳን ታማኝነት ያመለክታል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት (ሄስድ)።

▣ **"ከዘላለም እስከ ዘላለም"** ይህ የኦላም ድርብ ነው (ቢዲቢ 761፣ መዝ. 90:2)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (ኦላም)።

▣ **"ጽድቁም በልጅ ልጆች ላይ ነው"** ከመጀመሪያዎቹ የኦሪት መጻሕፍት (Pentateuch) እግዚአብሔር የአባቶችን ኃጢአት እስከ ሦስተኛና አራተኛና ትውልድ በልጆች ላይ እንደሚሻ እንረዳለን (ዘጸ. 20:5፤ ዘዳ. 5:9)። ሆኖም፣ ለሚወዱት ለእነርሱ ባርኮቶቹን እስከ ሺ ትውልድ ያደርጋል (ዘዳ. 5:10፤ 7:9)! በያህዌ ላይ የተጣለ እምነትና ታማኝነት በቤተሰብ ውስጥ ይራመዳል (ዘዳ. 4:9፤ 6:7፣20-25፤ 11:19፤ 32:46)፣ ኃጢአትና ዓመጻ እንደሚሆነው ሁሉ።

**103፡18 "የሚያደርጉአት"** መታዘዝ ለኪዳን ዓይነተኛ ነገር ነው። ሉዓላዊው አምላክ ያነሣሣዋል፣ ወሰንም ያበጅለታል፣ ነገር ግን ሕዝቡ ይታዘዙለት ዘንድ ይጠይቃል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ፤ ዘዳ. 4:2፣6፣9፣40፤ 5:10፣12፣29፣32፤ 6:2፣3፣17፣25፤ 7:8፣9፣11፣12)። ይህ ጽንሰ-ሐሳብ

ማለትም፣ የእግዚአብሔርን ቃል የመስማትና ቀጥሎም መታዘዝ የዕብራይስጥ ቃል ሼማ ነው (ቢዲቢ 1033፤ ዘዳ. 4:1፤ 5:1፤ 6:3፣4፤ 9:1፤ 20:3፤ 27:10፤ 33:7)። ኢየሱስ ይሄንኑ ተመሳሳይ ነጥብ ሉቃስ 6፡46 ላይ አድርጓል!

▣ **"ኪዳን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን።

---

***መዝሙር ፡ 103፡19-22***

**19እግዚአብሔር ዙፋኑን በሰማይ አዘጋጀ፥**
**መንግሥቱም ሁሉን ትገዛለች።**
**20ቃሉን የምትፈጽሙ፥ ብርቱዎችና ኃያላን፥**
**የቃሉንም ድምፅ የምትሰሙ መላእክቱ ሁሉ፥**
**እግዚአብሔርን ባርኩ።**
**21ሠራዊቱ ሁሉ፥ ፈቃዱን የምታደርጉ አገልጋዮቹ፥**
**እግዚአብሔርን ባርኩ።**
**22ፍጥረቶቹ ሁሉ**
**በግዛቱ ስፍራ ሁሉ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ።**
**ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ።**

---

**103፡19 "ሉዓላዊነቱ ሁሉን ትገዛለች"** "ሁሉም" የሚለው ቃል የሚጠቅሰው ለእግዚአብሔር የሚገባውን ምስጋና ነው፣ በፍጥረቱ። እሱ ሠርቶታል፤ እሱ ያመሰግነዋል፣ ሕይወት ያለውም ሆነ ሕይወት የሌለው።

**103፡20 "መላእክቱ ሁሉ እግዚአብሔርን አመስግኑ"** ይህ የሚገልጸው አካላዊ ሕያው የእግዚአብሔርን አገልጋዮች ነው። "ሠራዊቱ" በሚለው ቃል ላይ አንዳንድ ውይይቶች ተደርገዋል፣ (ቢዲቢ 838) መዝ. 103:21 ላይ፣ እሱንም አንዳንዶች እንደ ሌላ የመላእክት ቡድን የሚመለከቱ። ቃሉ ዘወትር የሚለው "ሠራዊት" ነው። ሆኖም፣ ሕይወት በሌላቸው ምስጋና ሳቢያ፣ መዝ. 103፡22 ላይ ባለው፣ ሌሎች "ሠራዊቱ"ን የሚመለከቱት ኮከባማውን ሰማያት እንደሚጠቅስ ነው (ዘዳ. 4:19፤ መዝ. 19:1-6)።

ታማኝ ተከታዮች ያህዌን መታዘዝ እንደሚኖርባቸው ሁሉ፣ እንዲሁ ደግሞ መላእክትም መታዘዝ ይኖርባቸዋል (ዕብ. 1፡6-14)።

**103፡22** ፍጥረት ሁሉ፣ እንስሳት፣ ሰዎች፣ እና መላእክት እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ (ፊሊ. 2፡9-11)። ባርኮት እና ምስጋና ለፈጣሪ ይገባል (መዝሙር 104) እና ለአዳኝ (መዝሙር 103) ከሁሉም! እኔም የግዴን እጠብቃለሁ የዚህ ታላቅ ኅብረ-ዘማሪ አባል ለመሆን (ራዕ. 5፡9-14)!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የዚህ መዝሙር ማዕከላዊ ጭብጥ ምንድነው?
2. ይህ መዝሙር ከመዝሙር 104 ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?
3. ፈውስ የተለየ ተስፋ ነውን፣ በክርስቶስ ማስተሠረያ? (ኢሳ. 53፡5)
4. ኪዳኑ ሁኔታዊ ነው ወይስ ሁኔታዊ ያልሆነ? አብራራ።

# መዝሙር 104

## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር ክብካቤ ለፍጥረቱ ሁሉ<br><br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | ሉዓላዊውን ጌታ ማመስገን፣ ስለ ፍጥረቱና መጋቢነቱ | ውዳሴ ለአምላክ ለፈጣሪ | ፈጣሪን ስለማመስገን | ባለክብሩ ፍጥረት |
| | 104:1-2 | | | |
| 104:1-4 | | 104:1-4 | 104:1-4 | 104:1-2ሀ |
| | | | | 104:2ለ-4 |
| | 104:3-4 | | | |
| | 104:5-9 | | | |
| 104:5-9 | | 104:5-9 | 104:5-9 | 104:5-6 |
| | | | | 104:7-9 |
| | 104:10-13 | | | |
| 104:10-13 | | 104:10-13 | 104:10-12 | 104:10-12 |
| | | | 104:13-15 | 104:13-15 |
| | 104:14-18 | | | |
| 104:14-17 | | 104:14-23 | | |
| | | | 104:16-18 | 104:16-18 |
| 104:18-23 | | | | |
| | 104:19-23 | | | |
| | | | 104:19-23 | 104:19-21 |
| | | | | 104:22-23 |
| | 104:24-26 | | | |
| 104:24-26 | | 104:24-26 | 104:24-26 | 104:24 |
| | | | | 104:25-26 |
| | 104:27-30 | | | |
| 104:27-30 | | 104:27-30 | 104:27-30 | 104:27-28 |
| | | | | 104:29-30 |
| | 104:31-32 | | | |
| 104:31-35 | | 104:31-35 | 104:31-32 | 104:31-32 |
| | 104:33-35ለ | | | |
| | | | 104:33-35ለ | 104:33-35ለ |
| | 104:35ሐ-መ | | | |
| | | | 104:35ሐ-መ | 104:35ሐ |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙር 103 እና 104 ሥነ-መለኮታዊ ጥንድ መፍጠራቸው ግልጽ ነው። ይህም የመክፈቻውና መዝጊያው ቁጥሮች በትክክል ተመሳሳይ በመሆናቸው ይታወቃል ("ባርክ፣" ፒይል ተተኳሪ)። የዚህ ጥንድነት ጠቀሜታ በሁለት አጠቃላይ ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ሊሆን ይችላል፣ በእነዚህ መዝሙሮች። መዝሙር 103 የያህዌ ኪዳናዊ ፍቅር ነው፣ እንደ ተቤዢ፣ እና መዝሙር 104 እግዚአብሔርን እንደ ፈጣሪ ያሳያል (ኤሎሂም)። የእግዚአብሔር ስሞች በእነዚህ በሁለቱም መዝሙራት መግቢያ ላይ ይንጸባረቃል፣ ያህዌ በሚል፣ የእግዚአብሔር የኪዳን ስም፣ እና ኤሎሂም፣ የእግዚአብሔር አጠቃላይ ስም። አይሁድ የሚሉት

መዝሙር 103 ያህዌን የሚገልጸው በምሕረት ኪዳኑ ነው፣ እንዲሁም መዝሙር 104 ኤሎሂምን የሚገልጸው እንደ ፈጣሪ ነው። ይህም እጅግ የተሻለ ማብራሪያ ነው፣ የእነዚህ ቃላት፣ በእነርሱ ውስጥ የጄኢዲፒን ንድፈ-ሐሳብ ከመመልከት ይልቅ፣ ይኸውም እጅግ የታወቀው የ19ኛው ክፍለ ዘመን ሒስ ምንጭ ስለሆነው፣ (የዘፍጥረትን መግቢያ ተመልከት፣ በቀጥታ የድረ-ገጽ መስመር ላይ www.freebiblecommentary.org)።

ለ. ይህ መዝሙር እጅግ ተመሳሳይ ነው፣ ከግብፃውያን *የአቶን ውዳሴ ጋር* (ኤኤንኢቲ (ጥቅምጽ) ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ጽሑፎች) 369-371)፣ በአክሄናተን IV (1375-1357 ቅ.ል.ክ)። ምንም እንኳ ተመሳሳይነት ቢኖርም፣ ግልጽ የሆነ ልዩነትም አለ። እንደምናውቀው የጥበብ ሥነ-ጽሑፍ ከብዙ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ባህሎች ጋር የሚያያዝ ነው፣ እናም የሆነ ተብሎ ተመሳሳይነት ሊኖር ይችላል፣ በግብፃዊው የፀሐይ አምላክ ውዳሴ እና በፈጣሪ ተቤዢ አምላክ መካከል፣ መዝሙር 103 እና 104። ለጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ትይዩዎች ተመልከት

1. ኢቪፒ *የመጽሐፍ ቅዱስ ዳራ ሐተታ*፣ ገጽ 548-550
2. *የመጽሐፍ ቅዱስ ጠንካራ አባባሎች*፣ ገጽ 277-278
3. *የመጽሐፍ ቅዱስ አዲጋቾች (ጠጣር ነገሮች)*፣ ገጽ 239-240
4. *የጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ አስተሳሰብና ብኪ*፣ ገጽ 165-199

ሐ. ያልተለመደ ነገር የሚሆነው የእግዚአብሔር ንቁ ፍጥረታት (ፊሊ. 2፡10) ሁለቱም መላእክትና ሰዎች፣ አጽንዖት አለመሰጠታቸው ነው፣ መዝሙር 104 ላይ። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ የዕብራይስጡ ጽሑፍ መዝ. 104፡4 የተፈጥሮን ነገሮች እንዲያው የሚጠቅስ ይመስላል፣ መልአካዊውን ዓለም ሳይሆን። ሰብዓዊነት ባጭሩ ተጠቅሷል፣ መዝ. 104፡14 እና 23 ላይ፣ ነገር ግን እንደ ጎንኛ አገላለጽ፣ እንደ ዋነኛ ነጥብ ሳይሆን።

መ. ይህ መዝሙር የሚያንጸባርቅ የሚመስለው፣ በተወሰነ ደረጃ ዘፍጥረት 1ን ነው።

1. ቀን 1፣ ዘፍ. 1፡1፣ ሰማያት – መዝ. 104፡1-4
2. ቀን 2-3፣ ዘፍ. 1፡6-9፣ ምድር – መዝ. 104፡5-9
3. ቀን 3፣ ዘፍ. 1፡10-17፣ ምግብና ውኃ – መዝ. 104፡13-17
4. ቀን 4፣ ዘፍ. 1፡14-19፣ ፀሐይና ጨረቃ – መዝ. 104፡19-23
5. ቀን 5፣ ዘፍ. 1፡20-23፣ አዕዋፍ እና ዓሣ – መዝ. 104፡24-26
6. ቀን 6፣ ዘፍ. 1፡24-26፣ እንስሳትና ሰዎች – (ከላይ ሐን ተመልከት)
7. ቀን 6፣ ዘፍ. 1፡29-31፣ የእግዚአብሔር ክብካበቤ – መዝ. 104፡27-30
8. ቀን 7፣ ዘፍ. 2፡1-3፣ የሰባተኛ ቀን ዕረፍት – መዝ. 104፡31-34
9. ከ7ኛ ቀን በኋላ (ማለትም፣ የዘፍጥረት 3 ውድቀት) – መዝ. 104፡35

## የቃልና የሐረግ ጥናት

***መዝሙር ፡ 104፡1-4***

**[1]ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ**
**አቤቱ አምላኬ ሆይ፥ አንተ እጅግ ታላቅ ነህ**
**ክብርንና ግርማን ለበስህ።**
**[2]ብርሃንን እንደ ልብስ ለበስህ**
**ሰማይንም እንደ መጋረጃ ዘረጋህ**
**[3]እልፍኙን በውኃ የሚሠራ፥**
**ሰረገላውን ደመና የሚያደርግ፥**
**በነፋስ ክንፍም የሚሄድ፥**
**[4]መላእክቱን መንፈስ የሚያደርግ፥**
**አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል።**

**104፡1 "ነፍሴ ሆይ እግዚአብሔርን ባርኪ"** በዚህ መንገድ ነው ሁለቱም መዝሙር 103 እና 104 የሚጀምሩትና የሚጨርሱት (ማለትም፣ ፔይል ተተኳሪዎች)። እሱም ለእግዚአብሔር ምስጋና ነው፣ ከልዕለ-ፍጥረቱ አጠቃላይ (ከሰዎች፣ ዘፍ. 1፡26-27)።

▣ **"አቤቱ ጌታዬ አምላኬ ሆይ፣ አንተ..."** መዝሙር 104፡1 ሁለት የተጠናቀቁዎች አሉት፣ እግዚአብሔርን የሚገልጹ፣ ሰባት ያልተወሰኑ አንቀጾች ተከትለውት፣ የእርሱን ድርጊቶች የሚገልጹ።

1. አንተ እጅግ ታላቅ ነህ – ቢዲቢ 152፣ ኬቢ 178፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ዘዳ. 3፡24፤ 2 ሳሙ. 7፡22፤ 1 ዜና. 16፡25፤ መዝ. 35፡27፤ 40፡16፤ 48፡1፤ 70፡4፤ 86፡10፤ 96፡4፤ 145፡3፤ ሚል.1፡5
2. ለበስህ – ቢዲቢ 527፣ ኬቢ 519፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
   ሀ. ክብር (ቢዲቢ 217፣ ኢዮብ 40፡10፤ መዝ. 96፡6)
   ለ. ግርማ (ቢዲቢ 214፣ መዝ. 93፡1)

መዝሙር 104 2-4 የእርሱን ድርጊቶች ይዘረዝራል፣ የሰማያዊውን ዓለም በመነሻ ሲፈጥር።

1. ራሱን በብርሃን ሸፍኗል – ቢዲቢ 741፣ ኬቢ 813፣ *ቃል* አንቀጽ። መዝ. 36፡9፤ ዳን. 2፡22፤ 1 ጢሞ. 6፡16፤ ያዕቆብ 1፡17፤ 1 ዮሐንስ 1፡5

2. ሰማይን ዘርግቷል – ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ *ቃል* አንቀጽ፣ ኢዮብ 9:8፤ 37:18፤ ኢሳ. 40:22፤ 42:5፤ 45:12፤ ኤር. 10:12፤ ዘካ. 12:1
3. የላይኛውን እልፍኝ በውኃ የሚሠራ – ቢዲቢ 900፣ ኬቢ 1138፣ *ፒል* አንቀጽ
4. *ሠረገላውን* ደመና የሚያደርግ – ቢዲቢ 962፣ ኬቢ 1321፣ *ቃል* አንቀጽ
5. በነፋስ ክንፍም የሚሄድ – ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ *ፒል* አንቀጽ፣ 2 ሳሙ. 22:11፤ መዝ. 18:10
6. *መላእክቱን መናፍስት ያደረገ* – ቢዲቢ 793፣ ኬቢ 889፣ *ቃል* አንቀጽ
7. አገልጋዮቹንም የእሳት ነበልባል – ግሡ ከቁ. 6 እንደሆነ ይገመታል
   ሀ. የእሳት ነበልባል – ቢዲቢ 529፣ ኬቢ 521፣ *ቃል* አንቀጽ
   ለ. አገልጋዮች – ቢዲቢ 1058፣ ኬቢ 1661፣ *ፒል* አንቀጽ

**104፡2 "ብርሃንን እንደ ልብስ ለበስህ"** *መዝምራት* ላይ በየስፍራው ጠቃሹ ዘፍጥረት 1 ከመሆኑ የተነሣ፣ አንዱ ይህ የሚጠቅሰው ዘፍ. 1፡3-5 እንደሆነ ለመመልከት ይሻል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ራሱ ነው እየተገለጸ ያለው፣ ቅርጸ-ቢስ እና ባዶ መሬት ሳይሆን።

ብርሃን ተደጋጋሚ የመጽሐፍ ቅዱስ ጭብጥ ነው፣ የእውነት፣ የፈውስ፣ የራዕይ፣ እና የመልካምነት። እግዚአብሔር እሱን ይለብሰዋል፣ ለምድራችንም ይናገረዋል!

▣ ***"እንደ መጋረጃ ዘረጋ"*** ይህ የተለመደ ጥንታዊ የመካከለኛው ምስራቅ ጽንሰ-ሐሳብ ነው (ኢሳ. 42:5፤ ኢዮብ 9:8፤ መዝ. 104:2፤ ኤር. 10:12፤ 51:15፤ ዘካ. 12:1)። በግብፃውያን *የሙታን መጽሐፍ*፣ ሰማይ የሚገለጸው እንደ "ቆዳ" ነው። በሪግ ቬዳ ሰማይ የሚገለጸው እንደ "ተዘረጋ ቆዳ ዓይነት" ነው። ይህም በዘይቤአዊ መንገድ አነጋገር የሰማይ ጣርያ ነው (ማለትም፣ የዚህ ፕላኔት ከባቢ ዓየር) ከመሬት በላይ። እሱም የዘይቤ ቋንቋ ነው።

**104፡3*ሀ*** ይህ የሚናገረው በምድር የዓለት ንጣፍ ላይ ስለቆሙት ምሰሶዎች ነው (መዝ. 24:2፤ 104:5፤ ኢዮብ 38:4)፣ በበላዩም ሰማያት (ማለትም፣ ከባቢ አየር፣ ርጥበት የሚከማችበት) ያረፉበት (አሞጽ 9፡6)።

*ሆኖም*፣ ይህ ቁጥር ደግሞ የሚጠቅሰው እነዚህ ምሰሶዎች በውኃ ላይ የተመሠረቱ ነው፣ የሰማያት (ማለትም፣ ከባቢ አየር፣ ዘፍ. 1፡7)። ምናባዊ ምስያው አሻሚ ነው፣ እናም በጥሬው ሊወሰድ አይገባም። እባክዎትን የእኔን ሐተታ ይመልከቱ ዘፍጥረት 1-11 ላይ በቀጥታ ዌብ ሳይት መስመር ለዘፍጥረት 1-11 ዘውግ www.freebiblecommentary.org.

በዚህ ስፍራ ላይ ያህዌ ቤተ-መንግሥቱን/መቅደሱን ከከባቢ አየር ውኃዎች በላይ የፈጠረበትን በሚያብራራው ክፍል፣ አዲስ መጽሐፍ መጥቀስ እሻለሁ፣ በጆን ዋልተን፣ *የዘፍጥረት አንዱ የጠፋው ዓለም*፣ እሱም እጅግ የረዳኝ፣ ዘፍጥረት 1ን ለመተርጎም። እርሱ የሚያስረግጠው ዘፍጥረት 1 የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) መግለጫ ነው ያህዌ የሰማይ መቅደሱን ለመገንባቱ (ዕብ. 8:2፣5፤ 9:23-24)። እንደሚመስለኝ ይህ ጽሑፍም ስለ እርሱ ይናገራል።

ኤቢ የሚለው፣ ከግሡ ጋር በተያያዘ (ቢዲቢ 900፣ ኬቢ 1138) እና "መጋዘን" (ገጽ 34)፣ እናም ስንኙን የሚተረጉመው "ላዕላይ እልፍኙን በውኃ ላይ ያከማቸ" በሚል ነው። ኢዮብ 37፡9 ትይዩ ሊሆን እንደሚችል ተመልከት (ማለትም፣ "እልፍኝ")፤ እንዲሁም ኢዮብ 38፡22 ተመልከት።

▣ ***"ሰረገላውን ደመና የሚያደርግ፥"*** ሴፕቱዋጂንት ይሄንን የሚያደርገው መልአካዊ መናፍስትን እንዲያመለክቱ ነው፣ ይህንንም ዕብ. 1፡7 ይከተለዋል፣ ነገር ግን በዐውደ-ጽሑፍ የዕብራውያን ቋንቋ የሚያቀርበው እነዚህ እንዲያው ተፈጥሯዊ ነገሮች ናቸው፣ እግዚአብሔር ለራሱ ዓላማ የሚጠቀምባቸውና የሚቆጣጠራቸው (ኢሳ. 19፡1)። "ነፋስ" የሚለው ቃል፣ በሁለቱም በዕብራይስጥና በግሪክ ሊጠቅስ የሚችለው "ነፋስን፣" "እስትፋስን፣" ወይም "መንፈስን" ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እስትንፋስ፣ ንፋስ፣ መንፈስ።

ደመናት ባህላዊ ፍቻቸው የመለኮት መጓጓዣ ናቸው (ዳን. 7:13፤ ማቴ. 24:30፤ 26:64፤ ሐዋ. 1:9-11፤ ራዕ. 1:7)። ምስያው የሚጠቀሰው ለሼከናህ ደመና ለብኪ ዘጸአት ልምምድ ነው (ዘጸ. 13:21፣22፤ 14:19፣20፣24፤ 16:10፤ 19:9፣16፤ 24:15፣16፣18፤ 34:5፤ 40:34-38)፣ ይኸውም ለእግዚአብሔር ከሕዝቡ ጋር መገኘት ተምሳሌት ይሆናል።

▣ **"በነፋስ ክንፍም የሚሄድ"** ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ተመልከት፣ መዝሙር 18፡10 ላይ።

**104፡4** *ሥጋዊ* ፍጥረት (ማለትም፣ ነፋስ እና እሳት፣ መዝ. 148፡8) የያህዌ አገልጋዮች ናቸው (LXX፣ ዕብ. 1፡7 ላይ ተጠቅሰዋል፣ የአገልጋዮችን አካላዊ ገጽታ ሰውኛ ለማድረግ)። ይህ ቁጥር ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ "ተፈጥሯዊ መገለጥን" የሚጠቅስ አይደለም (መዝ. 19፡1-6)፣ ነገር ግን የያህዌ ወዳጃዊ ቅርበት ነው፣ ከሥጋዊ ፍጥረቱ ጋር፣ በተለይም ከዚህ ምድር። ሲ. ኤስ. ሊዊስ ምድርን የሚጠራት፣ "የተነካች ፕላኔት" በሚል ነው።

የዩቢኤስ *የማስታወሻ መጽሐፍ* (ገጽ 879) የተሻለ ስዕላዊ ገለጻ አለው፣ ለጥንታዊ ዕብራይስጥ የዚህ ምድር ምናባዊ ንብርብር።

1. ከላይ ያለ ሰማይ (የእግዚአብሔር መኖርያ ስፍራ)
2. ውኃ
3. ጠፈር (ጠጣር ንፍቀ-ክበብ ጣሪያ ከመስኮቶች ጋር፣ መዝ. 78:23፤ ሚል. 3:10)
4. ከባቢ አየር (ደመናት፣ ወፎች)
5. ምሰሶዎች ሰማያትን የደገፉ (መዝ. 104፡3)
6. ምድር (ዝርግ)
7. የምድር ምሰሶዎች፣ በጥልቁ ውስጥ (1 ሳሙ. 2፡8፤ መዝ. 75፡3)
8. ሲኦል ከምድር በታች

ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት ለ። ቁ. 4።

▣ **"እሳት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እሳት

**መዝሙር ፡ 104፡5-9**

[5]ለዘላለም እንዳትናወጥ ምድርን
 በመሠረትዋ ላይ መሠረታት።
[6]በጥልቅ እንደ ልብስ ከደንሃት፥
 በተራሮችም ላይ ውኆች ይቆማሉ።
[7]ከዘለፋህም ይሸሻሉ፥
 ከነጐድጓድህም ድምፅ ይደነግጣሉ
[8]ወደ ተራሮች ይወጣሉ፥ ወደ ቈላዎች
 ወዳዘጋጀህላቸው ስፍራ ይወርዳሉ
[9]እንዳያልፉትም ድንበር አደረግህላቸው
 ምድርን ይከድኑ ዘንድ እንዳይመለሱ።

**104፡5-9** ዘፍጥረት 1 ላይ ብቸኛው እግዚአብሔር ወደ ሕላዌ አምጥቶት ያልተጠቀሰው ነገር "ውኃ" ነው። ይህ አንዳ ይገልጻል፣ (መዝ. 104፡3 እንደሚያደርገው) እሱ ውኃን እንደሚቆጣጠር (ዘፍ. 1፡6-8፣ ከላይ ያሉት ውኆች፤ ዘፍ. 1፡9-10፣ ከታች ያሉት ውኆች)። ኢዮብ 38፡8-11 ሥነ-መለኮታዊ ትይዩ ያበጃል።

**104፡5** የእግዚአብሔር ፍጥረት ሥርዓት የተጠበቀ ነው (1 ዜና. 16:30፤ መዝ. 24:1-2፤ 2 ጢሞ. 2:19፤ ዕብ. 11:10)።
 ይኸው ተመሳሳይ ምናብ ለሚመጣው መሲሕ ጥቅም ላይ ውሏል (ማለትም፣ የማዕዘን ድንጋይ፣ 1 ቆሮ. 3:11፤ ኤፌ. 2:20፤ 1 ጴጥ. 2:6-8)።

ልዩ ርዕስ፡ የማዕዘን ድንጋይ

◘ **"ለዘላለም እንዳትናወጥ"** ምንም እንኳ መዝ. 102፡25-26 ስለሚያልፈው ዓለም ቢናገርም (ማቴ. 5:18፤ 24:35፤ 2 ጴጥ. 3:10)፣ ምድር ደግሞ እንደ ጽናት ተምሳሊት ጥቅም ላይ ትውላለች (መዝ. 78:69፤ 93:1፤ 96:10፤ መክ. 1:4)። "ሰማይና ምድር" በመደበኝነት ጥቅም ላይ ውለዋል፣ እንደ ሁለቱ ቋሚ ምስክሮች (ዘዳ. 4:26፤ 30:19፤ 31:28፤ 32:1)።

**104፡6** ይህ የቅኔ ስንኝ የሚያስረግጠው ምድርን ውኃ እንደሸፈናት ነው፣ በእግዚአብሔር የቃል ፍጥረት ድርጊት መጀመሪያ ላይ (ዘፍ. 1:2፤ መዝ. 33:6-7፤ ምሳ. 3:19-20፤ 8:24-25፣27-28)። የዘፍጥረት አጠቃላይ መግለጫ እግዚአብሔር እንዴት ነገሮችን እንደለየ ይገልጻል (ጨለማ — ብርሃን፤ ውኃ — ምድር፤ የጨው ውኃ — ንጹሕ ውኃ) እና እነርሱ እንዴት እንደተበጁ፣ ከምን እና ከራሳቸው፣ በጊዜ ሂደት እንዲቀጥሉና እንዲጎለብቱ።

◘ **"ጥልቅ"** ይህ ቃል በበርካታ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) የፍጥረት አፈ-ታሪኮች ላይ ሰውኛ (ዘይቤ) ሆኗል፣ የመጀመሪያውን ፍጥረት መመሰቃቀል ለማሳየት። ሆኖም፣ ሁለቱም ዘፍጥረት 1 እና መዝሙር 104፡6 ላይ እግዚአብሔር የውኃውን ቅጠ-ቢስነት ይቆጣጠር ነበር (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ውኆች)። እሱም የተነጠለ፣ ብቻውን የሆነ አሀድ አይደለም፣ ነገር ግን በእግዚአብሔር ቁጥጥር ሥር ነው። ምንም እንኳ በዚህ መዝሙር ላይ ከጥንታዊ አፈ-ታሪክ ጋር የሚጎዳኙ አንዳንድ ቃላት ቢኖሩም፣ መዝሙሩ ሁሉንም ጥንታዊ አፈ ታሪካዊ ሰዋዊዎችን ከእነዚህ ቃላት ላይ አስወግዷቸዋል (መዝሙር 74፡12-17)። የዘፍጥረትን መግቢያ ተመልከት፣ በቀጥታ ድረ-ገጽ መስመር www.freebiblecommentary.org.

**104፡7 "በተግሣጽህ"** ስሙ (ቢዲቢ 172) የሚያመለክተው አፍአዊ ትእዛዝን ወይም ቃልን ነው። ይህም ብኪ ላይ በሦስት ሁነቶች ጥቅም ላይ ውሏል።

1. የመነሻ ፍጥረት – መዝ. 18:13፣15፤ ኢሳ. 50:2 (ማለትም፣ ዘፍ. 1:9-10)
2. የኤርትራ ባሕር መከፈል ዘጸአት ላይ – መዝ. 78:13፤ 106:9
3. የፍርድ መገለጥ (ጊዜው አልተወሰነም) – መዝ. 9:5፣11፤ 9:21፤ ኢሳ. 17:13

"ነጎድጓድ" የሚለው (ቢዲቢ 947) ትይዩ መሆኑን ተገንዘብ (ኢዮብ 26:14፤ 37:4-5፤ መዝ. 18:13፤ 29:3)። ነጎድጓድ በዮሐንስ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ራዕይ ላይ ድምጽን ለመግለጽ

1. አራቱን እንስሳት፣ ራዕ. 6:1
2. ብርቱ መልአክ፣ ራዕ. 10:3-4
3. የተዋጁት፣ ራዕ. 14:2
4. ብዙ ሰዎችን፣ ራዕ. 19:6

◘ **"ከተግሣጽህም ይሸሻሉ"** ይህ የሚገልጸው የእግዚአብሔርን የንግግር ቃል ብርቱነት ነው (ዘፍጥረት 1፤ ኢሳ. 55፡11፤ ዕብ. 1፡3)። እሱም ደግሞ የእርሱ ቃል የሚያሳየው ነገሮችን ወደ ሕልውና ማምጣቱን ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን እነርሱ የተበጁትና መልክ የያዙት በእርሱ ቃል መሆኑን ነው፣ ከመነሻ ፍጥረት በኋላ።

◘ **"ከነጐድጓድህም ድምፅ ይደነግጣሉ"** ይህ የሚያስታውሰን የዘፍጥረትን ልምምድ ነው፣ የእግዚአብሔር ድምጽ እንደ ነጎድጓድ ሲገለጽ፣ በሕግ መስጠት ጊዜ፣ በሲና ተራራ (ዘጸ. 19:10-19)።

**104፡8-9 "ወዳዘጋጀህላቸው ስፍራ"** እነዚህ ሁለት ቁጥሮች የሚያመለክቱት እግዚአብሔር ፍጥረቱን እንደሚቆጣጠር ነው። የተዘጋጀ ዕቅድ አለ፣ ፍጥረት ሁሉ የሚከተለው። ይህ መሠረታዊ ርዕዮተ-ዓለም የምዕራባዊ፣ ሳይንሳዊ መግለጫ ዳራ ነው። ተፈጥሯዊ ሥርዓት አለ፣ ተለይቶ ሊታወቅ የሚችል፣ እግዚአብሔር በፍጥረት ላይ ካለው የፈጣሪነትና የጠባቂነት እጅ የተነሣ። ይህ በእግዚአብሔር ሕልውና የማነም ዶክትሪን አይደለም፣

እሱም እግዚአብሔር ምድርን ፈጠረ ከዚያም በኋላ ተዋት እንደሚለው ዓይነት። ይህ ንቁ፣ መጽሐፍ ቅዱሳዊ አካላዊነት የሚያስረግጠው እግዚአብሔር በየሴከንድ ሴከንዱ በፍጥረቱ ላይ እንደሚያገባው ነው።

**104፥9** መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ ገጾች አሉት፣ እግዚአብሔር እንደሚቆጣጠርና በቋሚነት የባሕሮችንና ወንዞችን/ሐይቆችን ልኬታ እንደሚወስን (ኢዮብ 38:8-10፤ መዝ. 74:15፤ ምሳ. 8:29፤ ኤር. 5:22)። ውኃ ከነጥፋት ኃይሉ ተገርቷል (ማለትም፣ ኢሳ. 43:2)።

**መዝሙር ፡ 104፥10-13**

**[10]ምንጮችን ወደ ቈላዎች ይልካል**
**በተራሮች መካከል ውኆች ያልፋሉ**
**[11]የዱር አራዊትን ሁሉ ያጠጣሉ፥**
**የበረሃ አህያዎችም ጥማታቸውን ይረካሉ።**
**[12]የሰማይም ወፎች በእነርሱ ዘንድ ያድራሉ፥**
**በድንጋዩ ስንጥቅ መካከልም ይጮኻሉ።**
**[13]ተራሮችን ከላይ የሚያጠጣቸው**
**ከሥራህ ፍሬ ምድር ትጠግባለች።**

**104፥10-17** የፍጥረት ሦስተኛው ቀን በዚህ መዝሙር ላይ ጎላ ብሎ ታይቷል። እሱም የተክሎች ፍጥረትና ውኃ መጠጣት ነው፣ ይኸውም ለሁለቱም ለሰዎችና ለእንስሳት ምግብ መሆኑን የሚያረጋገጥ (ኢዮብ 38፥39-41)። የዱር እንስሳት መዝ. 104፥10-13 ላይ ይብራራሉ፤ የቤት እንስሳት መዝ. 104፥14 ላይ፤ እና የሰው ልጅ መዝ. 104፥14-15 ላይ።

ተደጋጋሚዎቹን የአንቀጽ (ግሥ) አጠቃቀም ተገንዘብ፣ መለኮታዊ ድርጊትን ለማመልከት (መዝ. 104:2፣3፣4፣10፣13፣14)።

የተትረፈረፈው ምግብ የሚያሳየው የሌዋ. 26:1-13፤ ዘዳ. 28:1-13፤ መዝ. 1:2-3 መፈጸምን ነው! ፍጥረት ማለት እንዲህ እንዲሆን ነበር፣ እናም ከውድቀት በፊት እንደዚህ ነበር! ይህ የራዕይ 21-22 ምናባዊ ምስያ ነው (ማለትም፣ ገነት እንደ አዲሲቷ ዔድን)።

**መዝሙር ፡ 104፥14-17**

**[14]እንጀራን ከምድር ያወጣ ዘንድ**
**ለምለሙን ለሰው ልጆች ጥቅም፥**
**ሣርንም ለእንስሳ ያበቅላል።**
**[15]ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል፥**
**ዘይትም ፊትን ያበራል፥**
**እህልም የሰውን ጕልበት ያጠነክራል።**
**[16]የእግዚአብሔር ዛፎች እርሱም የተከላቸው**
**የሊባኖስ ዝግባዎች ይጠግባሉ።**
**[17]በዚያም ወፎች ይዋለዳሉ፥**
**የሽመላ ቤትም የእነርሱ ጎረቤት ነው።**

**104፥14 "ለምለሙን ለሰው የሥራ ጥቅም"** የሰው ልጅ የሚሠራ መሆኑን መመልከቱ አስደናቂ ነው፣ በሁለቱም ከውድቀት በፊት እና በኋላ (ዘፍ. 2፥15 እና 3፥17-19)።

**104፥15 "ወይን የሰውን ልብ ደስ ያሰኛል፥"** ወይን በእግዚአብሔር ስጦታዎች ዝርዝር ውስጥ ይታያል። መጽሐፍ ቅዱስ ወይንን አይኮንንም፣ ነገር ግን ወይንን ከመጠን ያለፈ መጠቀምን ይኮንናል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አልኮልና አልኮልን ያላግባብ መጠቀም።

▣ **"ዘይትም ፊትን ያበራል፥"** ማብራት" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 843 II) እዚህጋ ብቻ ነው የሚከሰተው፣ ብኪ ላይ። እሱም የሚጠቅሰው የወይራ ዘይትን ነው፣ ይኸውም በጥንቶቹ በመዋቢያ ቅባትነት ጥቅም ላይ የሚውል። እሱም ፊትና እጅ ላይ ይደረጋል፣ ለበዓል ዝግጅት ጊዜ (መዝ. 23:5፤ 92:10፤ 141:1፤ መክ. 9:8፤ ሉቃስ 7:46)።

**104፥17-18** ምንም እንኳ በተለያዩ አንጓዎች ላይ ቢገኙም (እንደ አአመመቅ) በቅኔው ላይ፣ ሁለቱም የሚገልጹት እግዚአብሔር ለእንስሳት ስለ ሰጣቸው ቤቶች ዓይነት ነው። ይህ መዝሙር የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ክብካቤና መጋቢነት ነው፣ ለእንስሳት ለፍጥረቱ።

**104፥17 "ዝግባ ዛፎች"** ይህን ትርጉም አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ቅጅዎች ይከተሉታል። አእመቅ፣ የተእመቅ፣ እና አኢመቅ ማሻሻውን ይደግፋሉ (የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት እንዳደረገው ["ሐ" ደረጃ ይሰጣል] ለኤምቲ "በእነርሱ ላይም" ለሚለው፣ [ማለትም፣ የሊባኖስ ዝግባ ላይኛ ክፍል])!

**መዝሙር ፡ 104፥18-23**

**[18]ረጃጅም ተራራዎች ለዋላዎች፥**
**ድንጋዮችም ለእሽኮኮች መሸሻ ናቸው።**
**[19]ጨረቃን ለጊዜዎች አደረገ**
**ፀሐይም መግቢያውን ያውቃል።**

[20]**ጨለማ ታደርጋለህ ሌሊትም ይሆናል**
**በእርሱም የዱር አራዊት ሁሉ ይወጡበታል።**
[21]**የአንበሳ ግልገሎች ለመንጠቅ ይጮኻሉ፥**
**ከእግዚአብሔርም ምግባቸውን ይሻሉ።**
[22]**ፀሐይ ስትወጣ ይሰበሰባሉ**
**በየዋሻቸውም ይተኛሉ።**
[23]**ሰው ወደ ተግባሩ፥**
**እስኪመሽም ድረስ ወደ ሥራው ይወጣል።**

**104፡19 "ጨረቃን ለጊዜዎች አደረገ**
***ፀሐይም መግቢያውን ያውቃል።"*** ይህ የሚያንጸባርቀው የፍጥረትን አራተኛ ቀን ነው፣ እሱም ዓይነተኛውን እውነት ያመላክታል፣ እግዚአብሔር ፀሐይና ጨረቃን እንደሚቆጣጠር (ዘፍ. 1፡14-19)፣ እንዲሁም ብርሃንንና ጨለማን (ዘፍ. 1፡3-5)። ይኸም እንደ ጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አፈ-ታሪክ አይደለም፣ ድል ወይም ተቃርኖ፣ በብርሃንና በጨለማ ኃይላት መካከል፣ ነገር ግን የሚያሳየው እግዚአብሔር ሁሉንም እንደሚቆጣጠር ነው። ይህ እጅግ ጠቃሚ መግለጫ ነው ከባቢሎናውያን ኮከብ ቆጠራ አምልኮ አኳያ፣ እንዲሁም ከዘመናችን የሖሮስኮፕ አፈ-ታሪክ (መዝ. 19፡1-6)።

ብርሃናት (ማለትም፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ) ዘፍ. 1፡14 ላይ ተሰጥተዋል፣ የአምልኮ ጊዜያትን ለማሳየት (ማለትም፣ ሰንበት፣ ዓመታዊ የበዓል ቀናት፣ አጽዋማት)። እነርሱ ለሰው ልጅ የአምልኮ ጊዜያት አገልጋዮች ናቸው። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ እነርሱ በቀዳሚነት ወቅቶችን አያመለክቱም፣ እስካልተያያዙ ድረስ

1. የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ርጥበታማና ደረቅ ወራት (መዝ. 104:10-17)
2. የተለያዩ እንስሳት የመመገቢያ ሰዓት (መዝ. 104:20-23)

እግዚአብሔር ፈጥሯል ይቆጣጠራልም፣ ብርሃንንና ጨለማን (መዝ. 74:16፤ አሞጽ 5:8)። እነርሱ አማልክት ወይም መላእክት አይደሉም፣ በሰው ሕይወት ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩ! እነርሱ የሥርዓታዊ፣ መደበኛ ፍጥረት ዑደታዊ እንቅስቃሴና ዕረፍት ማሳያ ገጽታዎች ናቸው።

**104፡20ሀ** ይህ የቅኔ ስንኝ ሁለት ግሦች አሉት፣ እነርሱም በዓይነታቸው ተጽዕኖዊ የሆኑ (ነገር ግን እንደ ተጽዕኖዊ አይተረጎሙም) እንደ እግዚአብሔር ያለፈ ድርጊት፣ በፍጥረት ላይ (ዘፍ. 1፡3-4)።

**104፡21-23** ምንም እንኳ እሱ በቅድሚያ ያልተለመደ ዓይነት ቢመስልም፣ እነዚህ ቁጥሮች እንዲያው መግለጫዎች ናቸው፣ የዱር አራዊት የምሽት ጊዜን ለምግባቸው መሰብሰቢያ እንደሚያውሉት፣ የሰው ልጅና ሌሎች እንስሳት የቀኑን ጊዜ ይጠቀማሉ፣ ምግባቸውን ለመሰብሰብ። ለዚህም ሌላ ተጨማሪ ሥነ-መለኮታዊ አንድምታ ያለው አይመስልም፣ ይህ ቀለል ያለ የፍጥረት መግለጫ በምድር ላይ ምርታማነትን ለመጠቀም ሁነኛውን ሰዓት ከማካፈሉ በተቀር።

## መዝሙር ፡ 104፡24-26

[24]**አቤቱ፥ *ሥራህ* እጅግ ብዙ ነው**
**ሁሉን በጥበብ አደረግህ፥**
**ምድርም ከፍጥረትህ ተሞላች**
[25]**ይህች ባሕር ታላቅና ሰፊ ናት**
**በዚያ ስፍራ ቍጥር የሌለው ተንቀሳቃሽ፥**
**ታላላቆችና ታናናሾች እንስሶች አሉ።**
[26]**በዚያ ጊዜ መርከቦች ይሄዳሉ፥**
**በዚያም ላይ የፈጠርኸው ዘንዶ ይጫወትበታል።**

**104፡24 "ሁሉን በጥበብ አደረግህ፥"** ይህ የምሳ. 8፡22-31 ጠቃሽ ይሆናል፣ እሱም ሰውኛ የሆነው "ጥበብ" በፍጥረት የያህዌ ወኪል መሆኑ (ምሳ. 3፡19)።

◘ **"ምድርም ከፍጥረትህ ተሞላች"** ይህ የሚያመለክተው ሕይወት ያላቸውን ፍጥረታት ነው በምድር ላይ የተራቡት፣ በከፊልም የውኃ ፍጥረታት (መዝ. 104:25-26)።

"ሙብት" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 889) በበርካታ መንገዶች ይተረጎማል።

1. አአመመቅ አኪጀት፣ አእቅ፣ አኢመቅ፣ የተእመቅ – ሙብት (ጥሪት)
2. አአመመቅ ጎዳግ፣ አየተመቅ – ፍጥረታት
3. ጀፒኤስኦኤ – ፍጥረታት
4. LXX – ይዞታ
5. ኪጀት፣ ፔሺታ– ብልጽግና
6. ኖክስ – የመፍጠር ኃይልህ

ኤምቲ የነጠላ ቁጥር ነው ያለው፣ ነገር ግን የወል ስም ሊሆን ይችላል።

**104፡26 "በዚያም ላይ የፈጠርኸው ዘንዶ ይጫወትበታል።"** እግዚአብሔር ከፈጠራቸው እንስሳት ጋር ይጫወታል። በዑጋሪታዊ ሥነ-ጽሑፍ (ማለትም፣ የራስ ሻምራ ጽሑፎች) ልዕለ አማልክቱ፣ ኤል፣ ከባሕር ዘንዶ ጋር ይጫወታል፣ *ሎቶን* (ሌዋታን በዕብራይስጥ)። ግልጽ የሆነ ግንኙነት አለ፣ በብኪ ምናባዊ ምስያ እና በዑጋሪት (ማለትም፣ ከነአናዊ) አፈ-ታሪክ መካከል። እንደሚመስለኝ የብኪ ደራስያን የታወቁትን ጽንሰ-ሐሳቦች፣

ምስያዎች፣ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) የመራባት አማልክት ታሪኮችን ይጠቀማሉ፣ የያህዌን የተለየነትና ግርማ ለማስረገጥ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት።

"ሌዋታን" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ 531) የሚያመለክተው ጥንታዊ፣ ትልቅ የባሕር ዘንዶ ሲሆን፣ "ብሄሞት" የሚለው ቃል ግን (ቢ.ዲ.ቢ 97፣ ኢዮብ 40:15) የሚያመለክተው ጥንታዊ የየብስ (ምድር) ዘንዶ ነው (መዝ. 74:13፣14፤ ኢዮብ 3:8፤ 41:1፤ ኢሳ. 27:1)። ሌዋታን ላይ ለተሟላ ማስታወሻ ኢሳ. 27:1 ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ተመልከት።

የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 1398) የሚጠቅሰው አንዳንድ ሊቃውንት "ሌዋታን" የሚለውን ቃል የሚመለከቱት በጥሬ መልኩ ነው "ተጓዳኝ" በሚል — ዶልፊን ወይም ትልቅ አሳ፣ ዘወትር ከመርከብ አጠገብ የሚገኝ።

**መዝሙር ፡ 104፡27-30**

**27ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸው ዘንድ**
**እነዚህ ሁሉ አንተን ተስፋ ያደርጋሉ።**
**28በሰጠሃቸውም ጊዜ ይሰበስባሉ**
**እጅህን ትከፍታለህ፥ ከመልካም ነገርም ይጠግባሉ።**
**29ፊትህን ስትሰውር ይደነግጣሉ**
**ነፍሳቸውን ታወጣለህ ይሞታሉም፥**
**ወደ አፈራቸውም ይመለሳሉ።**
**30መንፈስህን ትልካለህ ይፈጠራሉም፥**
**የምድርንም ፊት ታድሳለህ።**

**104፡27-28 "አንተን ተስፋ ያደርጋሉ"** ይህ የእግዚአብሔርን ክብካቤና መጋቢነት ያሳያል፣ እስትንፋስ ላለው ፍጡር ሁላ (ዘፍ. 1:29-30፤ ቆላ. 1:17)።

**104፡29-30** ይህ የሚታወቅ ሐቅ ነው፣ አሮጌ መሞቱ (ዘፍ. 3:19፤ ኢዮብ 10:9፤ መዝ. 90:3) እና ታዳጊዎች መወለዳቸው፣ እነርሱን ለመተካት። ይህ ግልጽ ጠቃሽ ነው፣ የሰው ልጅ ከምድር አፈር ለመሠራቱ እና እግዚአብሔርም የሕይወትን እስትንፋስ እንደተነፈሰበት (ዘፍ. 2፡7)።

ሆኖም፣ አስገራሚ የሆነው፣ ሰው ኔፊሽ መሆኑ ነው (ቢ.ዲ.ቢ 659) ዘፍ. 2፡7 ላይ፣ ፍችውም "ነፍስ ሕይወት።" ይህ ቃል ኔፊሽ ደግሞ ጥቅም ላይ የዋለው እንስሳትን ለመጥቀስ ነው፣ ዘፍጥረት ላይ (ዘፍ. 1:24፤ 2:19)። ማስታወሻ ድረ-ገጽ ላይ ተመልከት ዘፍ. 35:18።

▣ "መንፈስ" የሚለውን ድርብ አጠቃቀም ተገንዘብ (ማለትም፣ "እስትንፋስ፣" ቢ.ዲ.ቢ 924፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ)።

1. የሰው መንፈስ ወይም የሕይወት ኃይል
2. የእግዚአብሔር መንፈስ (ወይም "እስትንፋስ" የዘፍ. 2፡7)

ብኪ ላይ "መንፈስ" ከእግዚአብሔር የሆነ ኃይል ነው፣ እሱም ዓላማውን የሚያስፈጽም (ማለትም፣ ዘፍ. 1፡2)፣ ነገር ግን አኪ ላይ ጽንሰ-ሐሳቡ አካል ይሆናል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመንፈስ አካላዊነት)።

**መዝሙር ፡ 104፡31-35**

**31የእግዚአብሔር ክብር ለዘላለም ይሁን**
**እግዚአብሔር በሥራው ደስ ይለዋል።**
**32ምድርን ያያል እንድትንቀጠቀጥም ያደርጋል**
**ተራሮችን ይዳስሳል ይጤሳሉም።**
**33በሕይወቴ ሳለሁ ለእግዚአብሔር እቀኛለሁ፥**
**ለአምላኬም በምኖርበት ዘመን ሁሉ እዘምራለሁ።**
**34ቃሌ ለእርሱ ይጣፍጠው፥**
**እኔም በእግዚአብሔር ደስ ይለኛል።**
**35ኀጥኣን ከምድር ይጥፉ**
**ዓመፀኞች እንግዲህ አይገኙ።**
**ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኪ።**
**ሃሌ ሉያ።**

**104፡31-32** በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች መዝ. 104፡31-32ን የሚመለከቱት እንደ ተለየ አንጓ ነው (ማለትም፣ አኪጀት፣ አእቅ፣ አኢመቅ፣ የተእመቅ)። ይህ የሰባቱ ቀን ፍጥረት ማጣቀሻ ነው። ሁለት ሰዋሰዋዊ ገጽታዎች አሉ፣ እነዚህ ቁጥሮች ላይ።

1. መዝ. 104:31 ሁለት ተጽዕኗዊዎች አሉት
   ሀ. የእግዚአብሔር ክብር ለዘላለም ይሁን – ቢ.ዲ.ቢ 224፣ ኬቢ 243፣ *ቃል* ተጽዕኗዊ፣ መዝ. 86:12
   ለ. እግዚአብሔር በሥራው ደስ ይለዋል – ቢ.ዲ.ቢ 970፣ ኬቢ 1333፣ *ቃል* 1Mየተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ ዘፍ. 1:3
2. መዝ. 104:32 ""እሱ..." በሚል ይጀምራል (አንቀጽ)፣ በዚህ መዝሙር መጀመሪያ ላይ የተለመደ የሆነ (ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 104፡1 ላይ)

**104፡32** ይህ ቋንቋ ጥቅም ላይ የዋለው ለመለኮት መገለጥ (ቲዎፋኒ) ነው። በትክክል ከዘፍጥረት 1 ጋር እንዴት እንደሚገጥም ርግጠኝነት የለም እሱም ዘወትር የሚዘመደው ከውድቀት በኋላ ላለው ጊዜ ነው፣ ኃጢአተኛው ዓለም በቅዱሱ ፈጣሪ አምላክ መገኘት ሲናወጥ!

**104፡33-34** በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች መዝ. 104፡33-35ለን የሚመለከቱት እንደ ተለየ አንጓ አድርገው ነው (ማለትም፣ አኪጀት፣ አእቅ፣ አኢመቅ፣ የተእመቅ)። ይህም የሆነበት ምክንያት

1. መዝ. 104:33 ሁለት ተጓዳኞች አሉት
2. መዝ. 104:34-35ለ ሁለት ቃል ያልተጠናቀቁዎች አሉት፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ (እና ሦስተኛው አንድምታዊ፣ መዝ. 104:35ለ)

አንዱ እግዚአብሔርን ሊያመሰግን ይችላል በቃል፣ በሐሳብ፣ እና ሕይወት ወይም አንዱ ሊጠፋ ይችላል (ቢዲቢ 1070፣ ኬቢ 1752) እና ሊደመሰስ ("ዳግም ላይገኝ፣" ኢዮብ 24:24፤ መዝ. 37:10)። ዘላለማዊ ውጤቶች ሊኖሩ ይችላሉ፣ በጊዜው በተደረጉ ምርጫዎች!

ሁነኛው የፍጥረት ባርኮት እና ሰላም በሰው ኃጢአት እና ዓመጸኝነት ተዘግቷል (ማለትም፣ ዘፍጥረት 3)። እግዚአብሔር በመነሻው የፈጠረው ይመለሳል (ዘፍጥረት 1-2ን ከራዕይ 21-22 ጋር አነጻጽር)።

**104፡35ሐ-መ** የዚህ መዝሙር መደምደሚያ ከመዝሙር 103 ድርብ ተተኳሪዎች ጋር ይገጥማል (ሁለት ፔይል ተተኳሪዎች፣ "ባርክ")። እዚህ

1. ባርክ – ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ ፒል ተተኳሪ
2. አመስግን – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ፒል ተተኳሪ፣ መዝ. 105:45፤ 106:48

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙር 103 እና 104 የሚዛመዱት እንዴት ነው?
2. "ያህዌ" የሚለው ቃል ጠቀሜታው ምንድነው፣ እሱም "ጌታ" ተብሎ የተተረጎመው (ሁሉም በትልልቅ ፊደላት) እና ኤሎሂም፡ እሱም በእንግሊዝኛ "እግዚአብሔር" ተብሎ የተተረጎመ?
3. ይህ መዝሙር ዘፍጥረት 1ን የሚያንጸባርቀው እንዴት ነው?
4. የመላእክትና የሰዎች መገኘት በዚህ መዝሙር ላይ ለምን ተንኳሰሰ፣ የእንስሳት ሕይወት ከፍ ሲደረግ?
5. እግዚአብሔር ጨረቃንና ከዋክብትን መቆጣጠሩ በዚህ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ዐውደ-ጽሑፍ እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?
6. መዝ. 104፡33-34 ሌሎቹን ጠቃሚ የብኪ እውነት ክፍሎችን፣ ማለትም ስለ እግዚአብሔር ክብካቤ፣ በሁለቱም በዚህ ዓለምም ሆነ በቀጣዩ ሕይወት ያለውን እንዴት ያንጸባርቃል?
7. "መደምሰስ" የሚለውን ዘመናዊ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ አብራራ።

# መዝሙር 105
## የአዲሶቹ ትርጕሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የጌታ ድንቅ ሥራ በእስራኤል አኳያ<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | የጌታ ዘላለማዊ ታማኝነት | የአምላክ ታላቅ ሥራዎች ታሪክ፣ በሕዝቡ አኳያ | እግዚአብሔርና ሕዝቡ | የእስራኤል አስደናቂ ታሪክ |
| 105:1-7 | 105:1-6 | 105:1-6 | 105:1-6 | 105:1-3 |
| | | | | 105:4-5 |
| | | | | 105:6-7 |
| | 105:7-12 | 105:7-11 | 105:7-11 | |
| | | | | 105:8-9 |
| 105:8-15 | | | | |
| | | | | 105:10-11 |
| | | | | 105:12-13 |
| | | 105:12-15 | 105:12-15 | |
| | | | | 105:14-15 |
| | 105:13-15 | | | |
| | | | | 105:16-17 |
| | | | | 105:18-19 |
| 105:16-24 | 105:16-22 | 105:16-22 | 105:16-22 | |
| | | | | 105:20-21 |
| | | | | 105:22-23 |
| | | | | 105:24-25 |
| | | | | 105:26-27 |
| | 105:23-25 | 105:23-25 | 105:23-25 | |
| | | | | 105:28-29 |
| | | | | 105:30-31 |
| 105:25-36 | | | | |
| | | | | 105:32-33 |
| | 105:26-36 | 105:26-36 | 105:26-36 | |
| | | | | 105:34-35 |
| | | | | 105:36-37 |
| | | | | 105:38-39 |
| | | | | 105:40-41 |
| | | | | 105:42-43 |
| 105:37-45 | 105:37-41 | 105:37-42 | 105:37-42 | |
| | | | | 105:44-45 |
| | 105:42-45 | 105:43-45 | 105:43-45ለ | |
| | | | 105:45ሐ | |

### **የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙር 105 እና 106 ሥነ-መለኮታዊ ምድብ ይፈጥራሉ።

ለተጨማሪ ሐሳብ ያህል፣ ዘመናዊዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ተርጓሚዎች በርግጥ አያውቁትም፣ ለምን፣ እንዴት፣ ወይም መቼ መዝሙራት እንደታረሙ (ኤዲት እንደተደረጉ) ፣ እና በማን። ይህም በሁሉም የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ እውነት ነው። ሂደቱ ለእኛ ጠፍቶብናል። ስለዚህ፣ የግድ መቀበል ያሻል፣ ብዙ ቅድመ-ግምቶችና መላምቶች ዘመናዊዎቹን ንድፈ-ሐሳቦች እንዳስኬዱ፣ በካኖናዜሽን (በቅዱሳት መጻሕፍት መወሰን) ሂደት። እኔ በርግጠኝነት እና በፍጹም አረጋግጣለሁ፣ የቅዱሳን መጻሕፍትን ተመስጧዊነት (ሦስቱን ቪዲዮዎች ተመልከቱ www.freebiblecommentary.org፣ ላይ፣ የመጀመሪያው አንቀጽ)፣ ግን ደግሞ የአይሁድን የራሳቸውን ካኖን መረዳት እቀበላለሁ፣ እንዲሁም የጥንቷ ቤተ-ክርስቲያንን ውሳኔዎች፣ የትኞቹ መጻሕፍት መካተት እንደሚኖርባቸው።

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተመስጦ እና ልዩ ርዕስ፡ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ሴሚናር ማስተማሪያ መጽሐፍ፣ "መጽሐፍ ቅዱስ፣ "ካኖን፣" "The Bible፣ I "Canon፣" ገጽ 19፣ ቀጥታ ድረ-ገጽ at www.freebiblecommentary.org.

ለ. መዝሙር 105 የእግዚአብሔርን የፍቅር እና ጸጋ ድርጊቶች ይገልጻል፣ በኪዳኑ ሕዝቦች ሕይወት ውስጥ።

1. ለአባቶች መነሻ ጥሪ፣ መዝ. 105:1-7
2. የአባቶች ጉዞ ወደ ከነአን፣ መዝ. 105:8-15
3. አባት (ያዕቆብ) በግብፅ፣ መዝ. 105:16-24
4. እስራኤል ከግብፅ፣ መዝ. 105:25-36
5. እስራኤል ወደ ከነአን፣ መዝ. 105:37-45

ሐ. መዝሙር 106 የእስራኤልን ዓመጸኛ ምላሽ ክብር ማጣት ይገልጻል።

መ. በዚህ መዝሙር እና በ1 ዜና መዋዕል 16:7-46 መካከል ብዙ ተመሳሳይነቶች አሉ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 105፡1-7**

**[1]እግዚአብሔርን አመስግኑ ስሙንም ጥሩ፥**
**ለአሕዛብም ሥራውን አውሩ።**
**[2]ተቀኙለት፥ ዘምሩለት፥**
**ተአምራቱንም ሁሉ ተናገሩ።**
**[3]በቅዱስ ስሙ ተጓደዱ**
**እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ ይበለው።**
**[4]እግዚአብሔርን ፈልጉት ትጸናላችሁም**
**ሁልጊዜ ፊቱን ፈልጉ።**
**[5-6]ባሪያዎቹ የአብርሃም ዘር፥**
**ለእርሱም የተመረጣችሁ የያዕቆብ ልጆች ሆይ፥**
**የሠራትን ድንቅ አስቡ፥**
**ተአምራቱን የአፉንም ፍርድ።**
**[7]እርሱ እግዚአብሔር አምላካችን ነው**
**ፍርዱ በምድር ሁሉ ነው።**

**105፡1-7** ይህ መዝሙር እና ይህ አንጓ የያህዌን የተለየ ጥሪና ግንኙነት ያጎላል፣ ከአብርሃምና ከዘሩ ጋር። ያህዌ በብርቱ፣ ዓላማዊ መንገዶች ይሠራል፣ ራዕዩን ወደ ፍጻሜ ለማምጣት፣ በዚህ በአንድ ቤተ-ሰብ በኩል።

ይህ መዝሙር በርካታ ቃላትን ይጠቀማል፣ እነዚህን ድርጊቶች ለመግለጽ።

1. ድርጊቶቹን፣ መዝ. 105:1 – ቢዲቢ 760፣ 1 ዜና. 16:8፤ መዝ. 9:11፤ 66:5፤ 77:13፤ 78:11፤ 103:7፤ ኢሳ. 12:4
2. ተአምራቱን ሁሉ፣ መዝ. 105:2 – ቢዲቢ 810፣ ዘጸ. 3:20፤ 34:10፤ ኢያ. 3:5፤ መሳ. 6:13፤ 1 ዜና. 16:9፣24፤ ኢዮብ 37:5፣14፤ መዝ. 9:1፤ 26:7፤ 78:11፤ 139:14፤ ኤር. 21:2፤ ሚኪያስ 7:15፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አስደናቂ ነገሮች
3. ተአምራቱን፣ መዝ. 105:5 – ቢዲቢ 810፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት ቁ. 2 ላይ
4. ድንቆቹን፣ መዝ. 105:5 – ቢዲቢ 68፣ ዘጸ. 7:3፤ 11:9፤ 1 ዜና. 16:12፤ ኢዮብ 3:3
5. ፍርድ፣ መዝ. 105:5 – ቢዲቢ 1048፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ
6. ፍርዶቹ፣ መዝ. 105:7 – ቢዲቢ 1048
7. ድንቅ ሥራዎቹ፣ መዝ. 105:27 – ቢዲቢ 68

የተለያዩ የእስራኤል የታሪክ ጊዜያት የእግዚአብሔርን ሥራዎች፣ በአብርሃም ቤተ-ሰብ በኩል ያደረገውን ያሳያሉ። የእነዚህ መለኮታዊ ድርጊቶች ዓላማ አሕዛብ እግዚአብሔርን እንዲያውቁ ለማገዝ ነው፣ 1 ነገ. 8፡42-43፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

መዝሙር 105፡1-5 ተከታታይ የሆኑ ተተኳሪዎች አሉት፣ ያህዌን በመቅደስ በማምለክ ስለሚደረግ ጸሎት።

1. ምስጋና አቅርቡ – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ሂፊል፣ 1 ዜና. 16:8፣34፤ ኢሳ. 12:4
2. ጥሩ – ቢዲቢ 894፣ ኬቢ 1128፣ ቃል፣ መዝ. 99:6

3. አሳውቁ – ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ ሂፊል፣ መዝ. 145:12
4. ዘምሩ – ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ ቃል
5. ምስጋና ዘምሩ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ፒል፣ መዝ. 66:2፤ 68:4፤ 135:3
6. ተናገሩ/አውሩ – ቢዲቢ 967፣ ኬቢ 1319፣ ቃል መዝ. 77:12፤ 119:27፤ 145:5፤ 147:1
7. ክብር – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ሂዝፓል
8. ፈልጉ – ቢዲቢ 205፣ ኬቢ 233፣ ዘጸ. 33:7፤ ዘዳ. 4:29፤ 1 ዜና. 16:10፤ 2 ዜና. 11:10-11፤ ኢሳ. 51:1፤ ኤር. 50:4፤ ሆሴ. 3:5፤ 5:6
9. ፈልጉ – ቢዲቢ 134፣ ኬቢ 152፣ ፒል፣ 1 ዜና. 16:11፤ 2 ዜና. 7:14፤ መዝ. 27:8፤ አሞጽ 4:5
10. አስቡ – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ ቃል 1 ዜና. 16:12

**105፡1 "ጌታ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ **"ስሙንም ጥሩ"** መዝሙር 105:1-4 የአምልኮ ሥርዓትን ይገልጻል (ሃይማኖታዊ ደንብ። "ስሙ" የሚወክለው የግለሰቡን ባሕርይ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ።

▣ **"ለአሕዛብም ሥራውን አውሩ"** እሱም የእግዚአብሔር ፍቃድ ነው፣ ምድር ሁሉ (መዝ. 105፡7ለ) እሱን እንዲያውቅ (መዝ. 145:12፤ ኢሳ. 12:4-5፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)። እስራኤል የዚህ ፍጻሜ አድራጊ ነበር መጽሐፍ ቅዱስም ስለዚህ መገለጥ የተመዘገበ ነው።

**105፡2 "ለእርሱም ዘምሩ"** ይህ (ቢዲቢ 967፣ ኬቢ 1319) ደግሞ የአምልኮ ሥርዓትን ይገልጻል። ስለ ያህዌ ይዘምራሉ፣ እና ስለ ማዳን ድርጊቱ።

▣ **"አውሩ"** ይህ በጥሬው "ማልዱ" ወይም "አሰላስሉ" ማለት ነው። እኛ የእግዚአብሔርን ባሕርይና ድርጊቶች በአእምሯችን ማሰላሰል ይገባናል (መዝ. 105:5፤ ዘዳ. 6:6-9)።

**105፡3 "መኳደድ"** ይህ ግሥ ፍችው መመካት ማለት ነው (ቢዲቢ 237)። እስራኤል በእግዚአብሔር "እንዲኳደዱ" ነበር፣ ለጠራቸውና በተለየ መልኩ አምላክ ለሆናቸው።

▣ **"እግዚአብሔርን የሚፈልግ ልብ ደስ ይበለው።"** "ልብ" የሚናገረው አጠቃላይ ስብዕናን ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ)። ምላሽ መስጠት ይኖርብናል (ግሡ ቃል ያልተጠናቀቀ ነው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ) ለእግዚአብሔር መነሻ ሥራ፣ እናም ተገቢው መንገድ "ደስታ" ነው (ቢዲቢ 970)።

**105:4**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀት፣** | |
| **አኢመቅ፣ አየተመቅ** | **"እና ኃይሉ"** |
| **አእቅ** | **"ለዕርዳታ"** |
| **LXX፣ Moffatt** | **"በርቱም"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ኃይሉ" (ታቦቱን የሚያመለክት፣ መዝ. 78:61፤ 132:8)** |
| **ፔሺታ፣ የተእመቅ** | **"ጠንክሩ"** |
| **አአመቅ** | **"ተማመኑ"** |
| **አእት መጽሐፍ ቅዱስ** | **"እሱ በሚሰጠው ብርታትም"** |

ከትርጉሞች ልዩነት በግልጽ እንደሚታየው፣ ሐረጉ ርግጠኛ አይደለም። እኔ የማስበው፣ ከመቅደስ አምልኮ ዐውደ-ጽሑፍ አኳያ (ማለትም፣ መዝ. 105:1-4)፣ የጀፒኤስአኤ ምርጫ እጅግ የተሻለ ነው (ማለትም፣ ታቦት፣ መዝ. 78:61፤ 132:8)።

▣ **"ሁልጊዜ ፊቱን ፈልጉ።"** ይህ ፈሊጣዊ መንገድ ነው፣ ለታማኝ ተከታዮች ጥሪ፣ ያህዌንና የእርሱን ራዕይ በአእምሯቸው ማሰላሰላቸውን እንዲቀጥሉ (ዘዳ. 6፡6-9)።

ይህ ከጳውሎስ ሳያቋርጡ መጸለይ አጽንዖት ጋር ተመሳሳይ ነው (ኤፌ. 6:18፤ 1 ተሰ. 5:16-18)።

**105፡5 "የአፉንም ፍርዶች"** ይህ የዕብራይስጡን ጽንሰ-ሐሳብ ያንጸባርቃል፣ የንግግር ቃልን ኃይል (ዘፍ. 1:1፤ ኢሳ. 55:1፤ ዮሐንስ 1:1፤ እና ማስታወሻ ዘፍ. 1:3 ላይ)። ለ"ፍርዶች" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር ራዕይ ቃላት።

**105፡6** ይህ ቁጥር የእግዚአብሔር አብርሃምን መምረጥ ያንጸባርቃል (መዝ. 105፡6ሀ) ዘሮቹንም (105፡6ለ) ለእርሱ የተመረጠ አገባብ (ዕቃ)፣ የሰው ልጆችን ሁሉ ለመዋጀት፣ ዘፍ. 3፡15።

በብኪ "የተመረጠ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 104፤ 1 ዜና. 16:13) ለዕቃነት ጥቅም ላይ እንደሚውል አስታውሱ (ማለትም፣ አገልግሎት)፣ ደኅንነት ሳይሆን። እግዚአብሔር አሕዛብን፣ ሕዝብን፣ እና ታሪካዊ ሁነቶችን ለመጠቀም ይመርጣል፣ ለትልቁ የመዋጀት ዕቅዱ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

**105፡7 "እሱ ጌታ አምላካችን ነው"** ይህ ሐረግ ዘጸ. 20፡2 ላይ ያለው የኪዳን ቋንቋ ጠቃሽ ሊሆን ይችላል። እሱም ሁለቱን የተለመዱ የመለኮት ስሞች ይዟል፣ ያህዌ — ጌታ እና ኤሎሂም — እግዚአብሔር። ዘመናዊዎቹ ምዕራባዊ አስተምህሮዎች የሚያስረግጡት፣ እነዚህ የሚወክሉት የመለኮት ስሞች በሁለት የተለያዩ የሰው የብኪ ደራሲያንን ነው። አይሁድ የሚያስረግጡት፣ እነርሱ የአንዱን እውነተኛ አምላክ ባሕርይ እንደሚወክሉ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት)። ኤሎሂም የመለኮት መጠሪያ ነው፣ እንደ ፈጣሪ፣ መጋቢ፣ እና ደጋፊ፣ ለሕይወት ሁሉ፣ ያህዌ ደግሞ የመለኮት የኪዳን ስም ነው እንደ አዳኝና ተቤዢ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ **"ፍርዶቹ በምድር ሁሉ ላይ ናቸው"** ይህ የእግዚአብሔርን ሁለንተናዊ (ዩኒቨርሳል) ትኩረት ያመለክታል፣ እሱም በዚህ የመዝሙራት ክፍል እጅግ ዋነኛ ሐሳብ የሆነ (ማለትም፣ መዝሙር 96፣ እዚያ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት)።

"ምድር" የሚለው ቃል "መሬት" በሚል ሊተረጎም ይችላል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር።

**መዝሙር ፡ 105፡8-15**

**8 ቃል ኪዳኑን ለዘላለም፥**
**እስከ ሺህ ትውልድ ያዘዘውን ቃሉን አሰበ፥**
**9 ለአብርሃም ያደረገውን፥**
**ለይስሐቅም የማለውን**
**10 ለያዕቆብ ሥርዓት እንዲሆን**
**ለእስራኤልም የዘላለም ኪዳን እንዲሆን አጸና።**
**11 እንዲህም አለ፦ ለአንተ የከነዓንን ምድር**
**የርስታችሁን ገመድ እሰጣለሁ**
**12 ይህም የሆነው እነርሱ በቍጥር ጥቂቶች ሰዎች፥**
**እጅግ ጥቂቶችና ስደተኞች ሲሆኑ ነው።**
**13 ከሕዝብ ወደ ሕዝብ፥**
**ከመንግሥታትም ወደ ሌላ ሕዝብ አለፉ።**
**14-15 የቀባኋቸውን አትዳስሱ፥**
**በነቢያቴም ክፉ አታድርጉ ብሎ፥**
**ሰው ግፍ ያደርግባቸው ዘንድ አልፈቀደም፥**
**ስለ እነርሱም ነገሥታትን ገሠጸ።**

**105፡8-15** ይህ አንዳ የያህዌን ጥሪ ይጠቅሳል፣ አብርሃምን፣ ዑርን ትቶ እሱን እንዲከተል፣ ወደ አዲሲቱ የተስፋይቱ ምድር (ማለትም፣ ዘፍጥረት 12-18)። ይኸው ተመሳሳይ ተስፋ ለያዕቆብ/እስራኤል ተረጋግጧል (ዘፍ. 28፡13-15)።

ያህዌ የአብርሃምን ዘሮች ጠብቋቸዋል፣ ደግፏቸዋልም፣ በከነአን በሚኖሩበት ጊዜ (ማለትም፣ ዘፍ. 12:7፤ 20:1-7፤ 35:5)።

**105፡8 "ቃል ኪዳኑን ለዘላለም አሰበ"** ከሞላ ጎደል ሁሉም የእግዚአብሔር ተስፋዎች ሁኔታዊ ናቸው፣ በሰዎች ምላሽ ላይ። ስለዚህ፣ "ዘላለም" የግድ መተርጎም ያለበት በሁኔታዊ/ሁኔታዊ ባልሆነ ኪዳን ዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (ኦላም)።

የመጽሐፍ ቅዱሳዊ ራዕይ ትኩረት፣ የእግዚአብሔር ታማኝነት ነው፣ የሰው ልጅ ባይሆን እንኳ (መዝሙር 105ን ከመዝሙር 106 ጋር አነጻጽር)። የወደቀው ሰው ልጅ ተስፋ በእርሱ የመፈጸም ችሎታ አይደለም፣ ምንም እንኳ ቀጣይነት ያለው የንስሐ እምነት ምላሽ አስፈላጊ ቢሆንም። የእግዚአብሔር የማይለወጥ ባሕርይ ነው ተስፋንና ዋስትናን የሚሰጠው (ሚል. 1፡6)።

ለ "ኪዳን" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን።

▣ **"እስከ ሺህ ትውልድ"** ይህ ፈሊጥ ነው ለእግዚአብሔር ታማኝነት። እሱም "ዘላለም" ከሚለው ጋር ትይዩ ነው፣ መዝ. 105፡8ሀ ላይ። እሱም በተቃርኖ ጥቅም ላይ ውሏል፣ በእግዚአብሔር ፍቅር እና ፍርድ መካከል፣ ዘዳ. 5፡9 እና 7፡9 ላይ።

"ሺህ" ተምሳሊታዊ ቁጥር ነው፣ በብዙ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሺህ (ዕልፍ) እና ልዩ ርዕስ፡ ተምሳሊታዊ ቁጥሮች በቅዱስ ቃሉ።

**105፡9-10** ያህዌ የመነሻውን ስለ መሬት ተስፋ ደግሞታል፣ ለአብርሃም ለሌሎቹም አባቶች።

1. አብርሃም – ዘፍ. 12:7፤ 13:15፤ 15:18
2. ይስሐቅ – ዘፍ. 26:3-4
3. ያዕቆብ/እስራኤል – ዘፍ. 28:13

**105:11** ይህ ጠቃሽ ነው የዘፍ. 12:1፤ 13:15፤ እና 15:18።

▣ **"የርስታችሁ ድርሻ"** ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር መዝ. 78:55 ላይ።

**105:12** የአብርሃም ቤተሰብ ሲጀምር ጥቂት ሆኖ ነው (ዘፍ. 34:30፤ 46:26-27፤ ዘዳ. 7:7፤ 1 ዜና. 16:19) ነገር ግን እንደ ሰማይ ከዋክብትና እንደ ባሕር ዳር አሸዋ በዝተዋል።

**"የቀባኋቸውን... ነቢያቴን"** እነዚህ በትይዩ ዝምድና አላቸው፣ እና ስለዚህ፣ አባቶችን ነው የሚጠቅሱት (ዘፍ. 20፡7)።

"የተቀቡት" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 603) የመሲሕ ሥር ፍቺ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሲሕ)። እሱም የሚያመለክተው አባቶችን ወይም ማኅበረሰቡን ነው፣ እግዚአብሔር የመረጠውና ያበቃው፣ ፍቃዱን ለመፈጸም።

**መዝሙር ፡ 105፡16-24**

**16 በምድር ላይ ራብን ጠራ፥**
**የእህልን ኃይል ሁሉ ሰበረ።**

17 **በፊታቸው ሰውን ላከ**
**ዮሴፍ ለባርነት ተሸጠ።**
18 **እግሮቹም በእግር ብረት ደከሙ፥**
**እርሱም በብረት ውስጥ ገባ።**
19 **ቃሉ እስኪመጣለት ድረስ፥**
**የእግዚአብሔር ቃል ፈተነው።**
20 **ንጉሥ ላከ ፈታውም፥**
**የአሕዛብም አለቃ አስፈታው።**
21 **የቤቱ ጌታ፥**
**የጥሪቱ ሁሉ ገዢ አደረገው፥**
22 **አለቆቹን እንደ ፈቃዱ ይገሥጽ ዘንድ፥**
**ሽማግሌዎቹንም ጥበበኞች ያደርጋቸው ዘንድ።**
23 **እስራኤልም ወደ ግብጽ ገባ፥**
**ያዕቆብም በካም አገር ተቀመጠ።**
24 **ሕዝቡንም እጅግ አበዛ፥**
**ከጠላቶቻቸውም ይልቅ አበረታቸው።**

**105፡16-24** ይህ አንጓ የሚገልጸው ያህዌ የኪዳን ሕዝቡን ከከነአን ወደ ግብፅ ሲመራ ነው። ይህ የእግዚአብሔር ዕቅድ ነበር።

1. የዮሴፍን እንደ መሪ ለማስነሣት፣ ማዘጋጀት፣ መዝ. 105፡17
2. እንቅስቃሴውን ለማስገደድ፣ በረሀብ ምክንያት፣ መዝ. 105፡16
3. ኋለኛውን ግጭት ለማድረግ፣ በግብፃውያንና በእስራኤላውያን መካከል፣ እናም ኃይሉ በግብፃውያን አማልክት ላይ ለማሳየት፣ እና ራሱን ለግብፃውያንና ለአካባቢው የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ሕዝቦች ለመግለጥ፣ መዝ. 105፡25

"በቁጥር ጥቂት" የሚለው መዝ. 105፡12 ከመዝ. 105፡24 ጋር ተቃርኗል።

**105፡16 "ጠራ... ሰበረ"** እግዚአብሔር ለዓላማው ጥፋትን ይጠቀማል፣ ኢሳ. 45፡7። ይህም ከመዝ. 105፡14-15 ጋር የሚቃረን ይመስላል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ሁለቱንም አዎንታዊና አሉታዊ ሁነቶችን ይጠቀማል። ይህም ግልጽ ነው፣ ከእስራኤል ጋር ባለው የኪዳን ግንኙነት (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-29፤ መዝሙር 1)። ሙሉውን ማስታወሻ ተመልከት ኢሳ. 45፡7 ላይ፣ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር።

◘ **"በትር እና እንጀራ"** ይህ ፈሊጥ በርካታ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏልኘ ብኪ ላይ (ሌዋ. 26:26፤ ሕዝ. 4:16፤ 5:16፤ 14:13)። እግዚአብሔር ዝናብ እና ምግብን ይቆጣጠራል። እሱ ለመባረክ ይፈልጋል፣ ነገር ግን ኃጢአትና ዓመጸኝነት ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑት ነገሮች እንዲያዙ ያደርጋል (ማለትም፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)። መዝምር 105 ላይ ረሀብ ነበር፣ መለኮታዊውን ዕቅድ ለማስፈጸም (ማለትም፣ ዮሴፍ ወደ ግብፅ የአመራር ስፍራ እና እስራኤል እዚያ እንዲኖር)።

"በትር" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 641) ሊያመለክት የሚችለው

1. የእህል አገዳ (ብር)
2. የእንጨት ዘንግ የምግብ መያዣ
3. የእንጨት ዘንግ የምግብ መያዣ፣ እንስሳት እንዳይበሉት
4. ተምሳሊታዊ መግለጫ መንገድ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) እንጀራ ለሕይወት ፍጹም አስፈላጊ መሆኑን ለመጥቀስ

**105፡17 "በፊታቸውም ሰው ላከ"** ይህ የሚያመለክተው ዮሴፍን ነው፣ የእግዚአብሔር መሣርያ የሆነበትን፣ የያዕቆብን የተመረጠ ቤተሰብ ለማዳንና ለመደገፍ (ዘፍጥረት 37፤ 39-46)። ዮሴፍ የእግዚአብሔርን ድርጊቶች የተገነዘበበት ስሜት ዘፍ. 45:4-8፤ 50:20 ላይ ተገልጿል። የእምነት ዓይኖች ታሪክን አጥርተው ያያሉ!

**105፡18 "እርሱም በብረት ውስጥ ገባ።"** ይህ የሚያንጸባርቀው የዮሴፍን የሥቃይ ልምምድ ነው፣ በገዛ ወንድሞቹ የተሸጠበትን፣ ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን እጅ ቢገነዘብም (ዘፍጥረት 37፤ 45፡4-8)።

ኤምቲ በጥሬው "ብረት መጣበት (ወደ እርሱ) ነፍስ።"

"መጣ" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) የተለመደ ግሥ ነው፣ በበርካታ ፍችዎች።

"ነፍስ" የሚለው ቃል *ኔፊሽ* ነው (ቢዲቢ 659)፣ እሱም ደግሞ ሰፊ የፍቺ መስክ ያለው፣ ነገር ግን በዚህ ዓለም ላይ አየር የሚተነፍሰውን ሕይወት ለመጥቀስ ነው (ማለትም፣ ሰው እና እንስሳ)።

አብዛኞቹ ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች የሚገምቱት ኔፊሽ የሚለው ቃል ተናባቢዎች፣ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ፣ የአካድያን ሥርን ያንጸባርቃል፣ "ጉሮሮ" ወይም "አንገት" (አየተመቅ፣ አእቅ፣ አኢመቅ፣ ጄፒኤስኦኤ፣ የተእመቅ)። ብረት እስርን መግለጫ መንገድ ነው (መዝ. 107፡ 10)።

ሆኖም፣ LXX ሐረጉን የሚተረጉመው እንደ "ነፍሱ በብረት ውስጥ አለፈች" በሚል ነው። የዮሴፍ የሕይወት ልምምድ፣ በወንድሞቹ የመጠላቱ እና በግብፃውያን እስር-ቤት የተቀበለው ጭካኔያዊ አያያዝ፣ እጅግ የሚያሠቃይና ጠባሳውን ትቶ ያለፈ ነበር። ነገር ግን እነርሱ ደግሞ ብርቱ፣ ታማኝ ተከታይ አፍርተዋል (ዕብ. 5፡8)።

**105፡19 "ጌታ ፈተነው"** እግዚአብሔር ልጆቹን ሁሉ ይፈትናል (አዳምና ሔዋን፣ ዘፍጥረት 3፤ አብርሃም፣ ዘፍ. 22፡1፤ ኢየሱስ፣ ማቴ. 4፡11)። ፈተና ማለት ለማበርታት ነው፣ ለማጥፋት ሳይሆን። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይፈትናል።

**105፡20 “ንጉሥ”** በርካታ ሊቃዊ (ምሁራዊ) አለመግባባት አለ፣ እስራኤል በግብፅ ከኖረባቸው ቀናት ጋር በተያያዘ እና የዘጸአት ቀናት። ዘመናዊዎቹ ሊቃውንት ርግጠኞች አይደሉም

1. የዘጸአትን ቀን
2. በዘጸአት የተካተቱትን እስራኤላውያን ቁጥር
3. የዘጸአት ፈርዖን
4. የዘጸአት የጉዞ መስመር

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘጸአት (ርግጠኝነት የሌላቸው)።

**105፡22** *መዝሙር* 105፡20-22 ከፈርዖን ጋር ይያያዛል። እሱም ለዮሴፍ ፈቅዶለታል፣ በገዛ ራሱ መሳፍንት እና ሽማግሌዎች ላይ ሥልጣን እንዲኖረው።

“እስር ቤት መጣል” የሚለው ቃል በጥሬው “መታሰር” ነው (ቢዲቢ 63፣ ኬቢ 75፣ *ቃል ያልተወሰነ አወቃቀር*)። እሱም ሕጋዊ ቃል ነው፣ ከ “ማሰር እና መፍታት” ጋር የሚያያዝ (ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት፣ ገጽ 380)።

ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ፣ ይህ ቃል፣ እሱም “እስረኛን ከማሰር፣” ጋር ነው የሚጠቀሰው፣ ብርቱ የሆነ ምናባዊ ምስያ ነው መዝ. 105፡18 የሚገልጸው፣ ነገር ግን ቃሉን አይጠቀምም። ሆኖም፣ ግልጽ የዎነ የቃላት መቀያየር (ጨዋታ) አለ፣ ግብፃውያን ዮሴፍን ማሰራቸው፣ አሁን ደግሞ እሱ እነርሱን ማሰሩ!

**104፡24** ይህ የሚያንጸባርቀው የብዙ ልጆችን መባረክ ነው፣ ዘጸ. 1፡7፣9 ላይ የታየው።

### መዝሙር ፡ 105፡25-36

**25ሕዝቡን ይጠሉ ዘንድ**
**በባሪያዎቹም ላይ ይተነኰሉ ዘንድ ልባቸውን ለወጠ።**
**26ባሪያውን ሙሴን**
**የመረጠውንም አሮንን ላከ።**
**27የተኣምራቱን ነገር በላያቸው**
**ድንቁንም በካም አገር አደረገ።**
**28ጨለማን ላከ ጨለመባቸውም**
**በቃሉም ዐመፁ።**
**29ውኃቸውን ወደ ደም ለወጠ፥**
**ዓሦቻቸውንም ገደለ።**
**30ምድራቸው የንጉሦቻቸውም ቤቶች**
**በጓጕንቸር ሞሉ።**
**31ተናገረ፥ የውሻ ዝንብ**
**ትንኝም በዳርቻቸው መጡ።**
**32ዝናባቸውን በረዶ አደረገው፥**
**እሳትም በምድራቸው ተቃጠለች።**
**33ወይናቸውንና በለሳቸውን መታ፥**
**የአገራቸውንም ዛፍ ሁሉ ሰበረ።**
**34ተናገረ፥ አንበጣም**
**ስፍር ቍጥር የሌለውም ኵብኵባ መጣ፥**
**35የአገራቸውንም ለምለም ሁሉ በላ፥**
**የምድራቸውንም ፍሬ በላ።**
**36የአገራቸውንም በኵር ሁሉ፥**
**የኍልበታቸውን መጀመሪያ ሁሉ መታ።**

**105፡25-36** *መዝ*. 105፡8-15 የአባቶችን ጊዜ እንደሚያንጸባርቅ፣ እንዲሁም *መዝ*. 105፡16-24 የዮሴፍን ልምምድ እንደሚያንጸባርቅ፣ *መዝ*. 105፡25-36 ዘጸአትን ያንጸባርቃል።

**105፡25 “ሕዝቡን ይጠሉ ዘንድ ልባቸውን ለወጠ”** እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ እንዳደነደነ፣ በሙሴ ጥያቄ ላይ፣ እሱ የግብፃውያን ሕዝቦች ልብ አደነደነ በአይሁድ ላይ። ቀጥሎ የእኔን ያልታተመ ማስታወሻ መደምደምያ፣ በዘጸ. 4፡21 ላይ አክያለሁ።

> **ዘጸ. 4፡21 “እኔ ግን ልቡን አደነድናለሁ፣ ሕዝቡም እንዲሄዱ አይፈቅድም”** እግዚአብሔር ለሙሴ ነግሮታል፣ በታላቅ ብርሃን መገኘት እንኳ፣ ዕብራውያን ቢያምኑም፣ ፈርዖን ግን ሊያምን አልቻለም። ይህ ምንባብ እና የእርሱ ተመሳሳይ የሆኑት ትልቅ ችግር በምዕራባዊ ሥነ-መለኮታውያን ላይ ፈጥረዋል። ይህ በዋነኛው ዐውደ-ጽሑፍ ይናገር ዘንድ መፍቀድ ይኖርብናል፣ ወደዚህ ምንባብም ጥያቄዎችን ማምጣት አይኖርብንም፣ ፈጽሞ ሊጠየቁ ወይም ሊብራሩ የማይገባቸውን። በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ)፣ በተለይም በእስራኤል እግዚአብሔር የሁሉም ነገር ምንጭ ነው (ኢዮብ 2፡10፤ መክ. 3፡28 ኢሳ. 45፡7፤ 54፡16፤ ሰቆ. 3፡37፤ ሕዝ. 14፡9፤ አሞጽ 3፡6ለ)። ስለዚህ፣ አይሁድ ምንም ችግር አይታያቸውም፣ እግዚአብሔር የፈርዖንን ልብ በማደንደኑ ወይም ፈርዖን የገዛ ራሱን ልብ በማደንደኑ። በተጨማሪዎቹ የአኪ መገለጦች እይታ ብቻ ላይ ነው፣ የሰው ልጅ ለእግዚአብሔር ምላሽ የመስጠት አስፈላጊነት፣ ማለትም የእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና የሰው ልጅ ነጻ ፍቃድ ችግር ምሥጢራዊ አያዎ (ፓራዶክስ) ለቤተ-ክርስቲያን የሚሆነው። ሁለቱንም እውነቶች ማስረገጡ ነው እጅግ የተሻለ የሚሆነው፣ አንዱን በሌላው ላይ ከማጉላት ይልቅ። በመጽሐፍ ቅዱስ እጅግ የተሻለው ስፍራ፣

በእነዚህ በሁለቱ መካከል ያለውን ዝምድና ለማስረገጥ፣ ሮሜ 9 በእግዚአብሔር ሉዓላዊነት እና ሮሜ 10 በሰው ልጅ ነጻ ፍቃድ ላይ። ዘጸአት ላይ ፈርዖን ልቡ የደነደነው በሦስት መንገዶች እንደሆነ ተገልጿል።

1. እግዚአብሔር ልቡን አደነደነ፣ ዘጸ. 4:21፤ 7:3፤ 9:12፤ 10:1፡20፡27፤ 11:10፤ 14:4፡8 (ሮሜ. 9:34)
2. ፈርዖን የገዛ ራሱን ልብ አደነደነ፣ ዘጸ. 8:15፡32፤ 9:34
3. ልቡ ደነደነ፣ ግን ምንጩ አልተጠቀሰም፣ ዘጸ. 7:13፡14፡22፤ 8:19፤ 9:7፡35

አስገራሚ የሚሆነው ደግሞ ይህን የልብ ድንደና ለመግለጽ ሦስት ግሦች ጥቅም ላይ መዋላቸው ነው።

1. "ጠንካራ መሆን" በስሜታዊነት መጠንከር በሚል መልኩ፣ ዘጸ. 4:21፤ 7:13፡22፤ 8:19፤ 9:12፡35፤ 10:20፡27፤ 11:10፤ 14:4፡8
2. "ከባድ መሆን" እና ስለዚህ፣ ምላሽ-ቢስ መሆን፣ ዘጸ. 7:14፤ 8:15፡32፤ 9:7፡34፤ 10:1
3. "ደንዳና መሆን" ዘጸ. 7:3

ሆኖም፣ እነዚህ ሁሉ ጥቅም ላይ የዋሉት በተመሳሳይ ዝምድና ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በአጽንዖት የሚያስተምረው እያንዳንዳችን ለድርጊታችን በግላችን ተጠያቂ መሆናችንን ነው፣ ፈርዖንና የአስቆሮቱ ይሁዳን ጨምሮ።

**105፡26** ያህዌ ሙሴን መጥራቱና መልሶ ወደ ግብፅ መላኩን የሚገልጸው ዘጸአት 3-4 ላይ ተመዝግቧል።

የአሮን አስፈላጊነት ዘጸ. 4፡10-17 ላይ ተገልጿል።

1. ዘጸ. 4፡10፣ የሙሴ ምላሽ (ሰበብ)
2. ዘጸ. 4፡11-12፣ የያህዌ ምላሽ
3. ዘጸ. 4፡13፣ የሙሴ ቀጣይ እምቢተኝነት
4. ዘጸ. 4፡14-16፣ የያህዌ ምላሽ፣ አሮንን ለመላክ፣ በእርሱ ምትክ እንዲናገርለት

**105፡27 "በካም ምድር"** ዕብራውያን እውቅና ይሰጣሉ፣ ግብፃውያን የጥንት ወንድሞች እንደሆኑ። ካም ደግሞ መዝ. 78:51፤ 106:22 ላይ ተጠቅሷል። ይኸም የሰውን ልጅ አንድነት ይገልጻል። ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት፣ ዘፍጥረት 10 ላይ።

**105፡28-36** ይህ የሚገልጸው መቅሠፍቱን ነው (ዘጸአት 7-11)። ሆኖም፣ ይህ ከፊል ዝርዝር ብቻ ነው። የሚጀምረውም በ9ኛው ነው፣ ከዚያም 1ኛ፣ 2ኛ፣ 4ኛ፣ 3ኛ፣ 7ኛ፣ 8ኛ፣ እና 10ኛ።

**105፡28** "በቃሉም ዐላመጹም" LXX እና ፔሺታ አሉታዊውን ገድፈውታል። ይኸም አየተመቅ እና የተእመቅ ይከተሉታል። ሆኖም፣ ኤቲ አሉታዊ አለው፣ እናም ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት መደምደሚያውን "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ)። ትርጓሜያዊው ጉዳይ "እነርሱ" የሚለው ማንን እንደሆነ ነው።

1. ኤምቲ – ሙሴ እና አሮን
2. LXX — ግብፃውያን፣ በተለይም ፈርዖን

**መዝሙር ፡ 105፡37-45**

**37ከወርቅና ከብርም ጋር አወጣቸው፥**
**በወገናቸውም ውስጥ ደዌ አልነበረም።**
**38ፈርተዋቸው ነበርና**
**ግብጽ በመውጣታቸው ደስ አላት።**
**39ደመናን ለመሸፈኛ ዘረጋባቸው፥**
**እሳትንም በሌሊት ያበራላቸው ዘንድ ዘረጋ።**
**40ለመኑ፥ ድርጭትንም አመጣላቸው፥**
**የሰማይንም እንጀራ አጠገባቸው።**
**41ዓለቱን ሰነጠቀ፥ ውኃውም ፈሰሰ**
**ወንዞች በበረሃ ሄዱ**
**42ለባሪያው ለአብርሃም የነገረውን**
**ቅዱስ ቃሉን አስቦአልና።**
**43ሕዝቡንም በደስታ**
**የተመረጡትንም በእልልታ አወጣ።**
**44የአሕዛብንም አገሮች ሰጣቸው፥**
**የወገኖችንም ድካም ወረሱ፥**
**45ሕጉን ይጠብቁ ዘንድ፥**
**ሥርዓቱንም ይፈልጉ ዘንድ።**
**ሃሌ ሉያ**

**105፡37-43** እነዚህ ቁጥሮች በምድረ በዳ የመንከራተትን ዘመን ያንጸባርቃሉ (ዘኁልቍ 13-36)።

**105፡37 "ከብርና ከወርቅ"** ግብፃውያን ብዙ ወርቅና ብር ለእስራኤላውያን ሰጥተዋቸዋል (ዘጸ. 3:21-22፤ 11:2፤ 12:35-36)። እሱም በያህዌ በውርደት መሸነፍን ማሳያ መንገድ ነው (መዝ. 105:38)።

▣ **"በወገኖቹም መሐል"** ይህ ሐረግ "በሠራዊታቸው" ከሚለው ጋር ሊያያዝ ይችላል (ቢዲቢ 838)፣ እሱም ዘጸ. 6፡26፤ 12፡51፤ እና ጆሴፈስ፣ አንቲክ. 14.6 ላይ የሚገኝ። እሱም ማለት፣ እስራኤላውያን ግብፅን ሲለቁ፣ በዘጸአታቸው ላይ፣ በየነገዳቸው ቡድን መስፈራቸውን ነው።

▣ **"በወገናቸውም ውስጥ የተሰናከለ አልነበረም"** ይህ የሚያሳየው የእግዚአብሔርን ልዩ ተአምራዊ ክብካቤ ነው፣ ለሽማግሌዎች፣ ለሕሙማን፣ እና ለታዳጊዎች (ዘዳ. 8፡4)።

**105፡39 "… ደመና…"** ይህ "*ሼኪናህ* የክብር ደመና" ተብሎ ይጠራል፣ በራቢዎች (ዘጸ. 13:21-22፤ 14:19፣24፤ 33:9-10፤ መዝ. 78:14፤ 99:7)። እሱም በርካታ ነገሮችን ለእስራኤላውያን አቀዳጅቷል።

1. የያህዌ አካላዊ መገኘት ተምሳሊት (*ሼኪናህ* "አብሮ መኖር" ማለት ነው)
2. እሱም እስራኤልን ከተመረጠው የፈርዖን ሠራዊት ለይቷል (ዘጸ. 14፡19-20)
3. እሱ እስራኤልን መርቷል (ዘጸ. 13:21-22፤ ዘኍ. 9:17-23)
4. እሱ ከሙቀት ይሸፍናቸው ይከላከላቸውም ነበር (መዝ. 105፡39)
5. እሱ በምሽት በሰፈሩ ላይ ያበራላቸው፣ ይልቁንም በምሽት እንዲጓዙ ያደርጋቸው ነበር (ዘጸ. 13:21፤ ነህ. 9:12፣19)
6. እሱም አሕዘብ እስራኤልን እንዲፈሩ አድርጎ ነበር (ዘጸ. 23:27፤ ዘዳ. 2:25፤ 11:25፤ ኢያ. 2:9)
7. በመጨረሻም እስራኤላውያን ዮርዳኖስን እንዳቋረጡ ጠፋ (ዘጸ. 16:35፤ ኢያ. 5:12)፣ ነገር ግን በሰሎሞን መቅደስ ምርቃት ላይ ዳግመኛ ተከሰተ (1 ነገሥት 8)።

**105፡40 "ለመኑ"** ኤምቲ "ለመነ" የሚል አለው። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 381) ለዚህ "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል (ሁነኛ ጥርጣሬ)። ጥያቄ የሚሆነው ተውላጠ ስሙ ማንን እንደሚያመለክት ነው።

1. ሕዝቡን ባጠቃላይ
2. ከመካከላቸው አንዱን፣ እንደ አፈ-ጉባኤ የሚሠራውን
3. ያህዌ ራሱ

▣ **"ድርጭት"** እግዚአብሔር የድርጭት *ሥጋ* ሁለት ጊዜ አቅርቧል (ዘጸ. 16:13-14 እና ዘኍ. 11:31) እንደ ፍቅር ምልክትና ለመስጠትና ለመንከባከብ እንደገባው ቃል።

▣ **"የሰማይ እንጀራ"** ይህ የመና ሌለኛው ስም ነው (ዘጸአት 16)።

ዘዳ. 8፡3 ላይ፣ ሕዝቡ "መና" ብለው ጠርተውታል (ቢ.ዲ.ቢ. 577 I፣ [ዘጸ. 16:31] ከጥያቄው፣ ዘጸ. 16:4፣ ላይ ካለው "ምንድነው?" ሙሴ "የሰማይ እንጀራ፣" ብሎ ጠርቶታል ዘጸ. 16:4)። እሱም የእግዚአብሔር የተለየ መንግብ ስጦታ ነበር፣ በምድረ-በዳ መንከራተት ዘመን። እሱም ዘጸ. 16:4፣ 14-15፤ 31፤ ዘኍ. 11:7-8 ላይ ተገልጿል፣ ነገር ግን ትክክለኛ ይዘቱ ለእኛ አልታወቀም (ቢ.ዲ.ቢ. የሚለው እሱ ለቤዶይን (ዘላን የዓረብ ነገዶች) ይታወቅ ነበር፣ ሲና ላይ፣ እናም እሱ የሆነ ተክል ጭማቂ ነው፣ ይህ ግን ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ገለጻ ጋር አይገጥምም)። እግዚአብሔር የሚያስፈልጋቸውን በየዕለቱ ይሰጣቸው ነበር፣ ለረጅም ጊዜ ሳይሆን፣ ስለዚህ ሕዝቡ በእርሱ መታመንን ይማሩ ነበር፣ በየዕለቱ ለሚያስፈልጋቸው። ይህንንም ደግሞ ለአዲስ ኪዳን አማኞች አድርጓል (ማቴ. 6፡11)።

**105፡41 "ዓለቱን ሰነጠቀ"** ይህ መለኮታዊ የውኃ ስጦታ በርካታ ጊዜ ተደግሟል (ዘጸ. 17:1-6፤ ዘኍ. 20:11፤ ዘዳ. 8:15፤ መዝ. 78:20፤ 114:8)። እሱም መሲሓዊ ተምሳሊት ሆኗል፣ 1 ቆሮ. 10:4 ላይ።

**105፡42 "ቅዱስ ቃሉን አስቦአልና።"** ይህ ሚያመለክተው የእግዚአሔርን መነሻ ኪዳን ነው፣ ከአብርሃም ጋር (መዝ. 105:5-6፤ ዘፍጥረት 12-15፣ በተለይም ዘፍ. 15:16)።

**105፡45 "ሕጉን ይጠብቁ ዘንድ፥**

**ሥርዓቱንም ይፈልጉ ዘንድ።"** መታዘዝ ለተገለጠ የእግዚአብሔር ቃል ዋነኛ ነገር ነው። መታዘዝ ልብን ይገልጣል። ኪዳን ሁለት ገጽታዎች አሉት።

1. የያህዌ ሉዓላዊነትና ታማኝነት (ዘዳ. 4፡39)
2. የሕዝቡ እምነትና ታዛዥነት (ዘዳ. 4:40፤ መዝ. 25:10፤ 103:18)
3. ያህዌ ታማኝ ነው (ዘዳ. 7፡9)፣ ስለዚህ፣ ሕዝቡም እንደዚሁ መሆን ይኖርባቸዋል!

▣ **"እግዚአብሔርን አመስግኑ"** ይህ በጥሬው "ያህን አመስግኑ" ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 237 II፣ ኬቢ. 248፣ *ፒል* ተተኳሪ ኪ*ያህ* ጋር፣ ቢ.ዲ.ቢ. 219)። በእንግሊዝኛ እሱ የሚተረጎመው "ሃሌሉያ" በሚል ነው። ይህ ሐረግ የተለመደ አዝማች ነው፣ በመጨረሻው የመዝሙር ክፍል (ማለትም፣ መዝ. 104:35፤ 105:45፤ 106:1፣48፤ 111:1፤ 112:1፤ 113:1፣9፤ 116:19፤ 117:2፤ 135:1፣21፤ 146:1፣10፤ 147:1፤ 148:1፣14፤ 149:1፣9፤ 150:1፣6)። እንዴት ተገቢ ነው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መጽሐፍ ቅዱስ በሕዝብ፣ በጋራ አምልኮ ላይ እንድንሳተፍ የሚያበረታታን ለምንድነው?
2. የአሀዳዊነት አንድምታዎች ምንድናቸው?
3. እግዚአብሔር ራብን ይልካልን? (መዝ. 105:16)
4. የእግዚአብሔር የፍቅርና የማዳን ድርጊቶች፣ እስራኤልን ወግኖ መደረጉ እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?
5. የእግዚአብሔር ኪዳናት ሁኔታዊ ናቸው ወይስ ሁኔታዊ ያልሆኑ?
6. መዝሙሩ "የመዳን ታሪክ" ለምን ተብሎ ተጠራ?

# መዝሙር 106
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእት** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| የእስራኤል ዓመጸኝነትና የጌታ አዳኝነት | ደስታ በእስራኤል ኃጢአት ይቅርታ | የአምላክ ታላቅ ድርጊት ታሪክ፣ በኃጢአት ንስሐና በዕርዳታ ጸሎት | የእግዚአብሔር መልካምነት ለሕዝቡ | የበደል ብሔራዊ ኑዛዜ |
| <u>ኤምቲ መግቢያ የለውም</u> | | | | |
| | | 106:1-3 | | |
| 106:1-3 | 106:1ሀ | | 106:1-3 | 106:1-2 |
| | 106:1ለ-3 | | | |
| | | | | 106:3-4ለ |
| | | 106:4-5 | | |
| 106:4-5 | 106:4-5 | | 106:4-5 | 106:4ሐ-5 |
| | | 106:6-12 | | |
| 106:6-12 | 106:6-7 | | 106:6-12 | 106:6-7ለ |
| | | | | 106:7ሐ-8 |
| | 106:8-12 | | | |
| | | | | 106:9-10 |
| | | | | 106:11-12 |
| | | 106:13-15 | | |
| 106:13-15 | 106:13-15 | | 106:13-15 | 106:13-14 |
| | | | | 106:15-16 |
| | | 106:16-18 | | |
| 106:16-18 | 106:16-18 | | 106:16-18 | |
| | | | | 106:17-18 |
| | | 106:19-23 | | |
| 106:19-27 | 106:19-23 | | 106:19-23 | 106:19-20 |
| | | | | 106:21-22 |
| | | | | 106:23 |
| | | 106:24-27 | | |
| | 106:24-27 | | 106:24-27 | 106:24-25 |
| | | | | 106:26-27 |
| | | 106:28-31 | | |
| 106:28-31 | 106:28-31 | | 106:28-31 | 106:28-29 |
| | | | | 106:30-31 |
| | | 106:32-33 | | |
| 106:32-33 | 106:32-33 | | 106:32-33 | 106:32-33 |
| | | 106:34-39 | | |
| 106:34-39 | 106:34-39 | | 106:34-39 | 106:34-35 |
| | | | | 106:36-37 |
| | | | | 106:38 |
| | | | | 106:39-40 |
| | | 106:40-43 | | |
| 106:40-43 | 106:40-43 | | 106:40-46 | |
| | | | | 106:41-42 |
| | | | | 106:43-44 |
| | | 106:44-46 | | |
| 106:44-46 | 106:44-46 | | | |
| | | | | 106:45-46 |
| | | 106:47 | | |
| 106:47-48 | 106:47 | | 106:47 | 106:47 |
| | | 106:48 | | |
| | 106:48ሀ-ሐ | | 106:48ሀ-ሐ | 106:48 |
| | 106:48መ | | 106:48መ | |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (**ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል**)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙር 105 ያህዌ አብርሃምንና ዝርዮቹን ያዳነበት/የታደገበት ታሪክ ከሆነ፣ እንግዲያውስ መዝ. 106 የእንርሱ ቀጣይነት ያለው ዓመጻ ታሪክ ነው። ያህዌ ታማኝ ነው፤ ሕዝቡ ግን ያልታመኑ ናቸው!

ለ. የዘጸአት፣ ሌዋውያን፣ ዘኍልቁ፣ ዘዳግም፣ እና የመሳፍንት መጻሕፍት የሚያተኩሩት በአብዛኛው ክፍል በታሪካዊ ጠቃሽ ላይ ነው። የእነርሱ ዝርዝር ይሄውና

1. መዝ. 106:7 – ዘጸ. 14:11-12
2. መዝ. 106:9 – ዘጸ. 14:21
3. መዝ. 106:10 – ዘጸ. 14:30
4. መዝ. 106:11 – ዘጸ. 14:28፤ 15:5
5. መዝ. 106:12 – ዘጸ. 14:31
6. መዝ. 106:13 – ዘጸ. 15:24፤ 16:2፤ 17:2
7. መዝ. 106:14 – ዘጸ. 17:2፤ ዘኍ. 11:4
8. መዝ. 106:15 – ዘኍ. 11:31
9. መዝ. 106:16 – ዘኍ. 16:3
10. መዝ. 106:17 – ዘኍ. 16:32
11. መዝ. 106:18 – ዘኍ. 16:35
12. መዝ. 106:19 – ዘጸ. 32:4፤ ዘዳ. 9:8
13. መዝ. 106:23 – ዘጸ. 32:10፣11-14፤ ዘዳ. 9:14፣25-29
14. መዝ. 106:24 – ዘኍ. 14:31፤ ዘዳ. 1:32፤ 9:23
15. መዝ. 106:25 – ዘኍ. 14:2፤ ዘዳ. 1:27
16. መዝ. 106:26 – ዘኍ. 14:28-35
17. መዝ. 106:27 – ዘዳ. 4:27
18. መዝ. 106:28 – ዘኍ. 25:2፣3፤ ዘዳ. 4:3
19. መዝ. 106:29 – ዘኍ 25:4
20. መዝ. 106:30 – ዘኍ. 25:7፣8
21. መዝ. 106:31 – ዘኍ. 25:11-13
22. መዝ. 106:32 – ዘኍ. 20:2-13
23. መዝ. 106:33 – ዘኍ. 20:3፣10
24. መዝ. 106:34 – መሳ. 1:21፣27-36፤ ዘዳ. 7:2፣16
25. መዝ. 106:35 – መሳ. 3:5፣6
26. መዝ. 106:36 – መሳ. 2:12
27. መዝ. 106:37 – ዘዳ. 12:31፤ 32:17
28. መዝ. 106:38 – ዘኍ. 35:33፤ ዘዳ 18:10
29. መዝ. 106:39 – ሌዋ. 17:7፤ 18:24፤ ዘኍ. 15:39፤ መሳ. 2:17
30. መዝ. 106:40 – ሌዋ. 26:30፤ ዘዳ. 32:19፤ መሳ. 2:14
31. መዝ. 106:41 – መሳ. 2:14
32. መዝ. 106:42 – መሳ. 4:3፤ 10:12
33. መዝ. 106:43 – መሳ. 2:16-18፤ 6:6
34. መዝ. 106:44 – መሳ. 3:9፤ 6:7፤ 10:10
35. መዝ. 106:45 – ሌዋ. 26:42፤ መሳ. 2:18
36. መዝ. 106:46 – 2 ዜና. 30:9፤ እዝራ 9:9፤ ነሀ. 1:11

ሐ. መዝሙር ላይ ዘወትር እንደሚሆነው ሁሉ፣ የነጠላና የብዙ ቁጥር መቀያየር ሊያያዝ የሚችለው ከአርታኢው ማቀያየር ጋር ነው፣ አንዱን ነጠላ መዝሙር ወደ አጠቃላይ/የአምልኮ ሥርዓታዊ መዝሙር በመቀየር።

# የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 106፡1-3**

**1ሃሌ ሉያ**
**ቸር ነውና፥**
**ምህረቱም ለዘላለም ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ።**
**2የእግዚአብሔርን ኃይል ሥራ ማን ይናገራል?**
**ምስጋናውንስ ሁሉ ማን ያሰማል?**
**3ፍርድን የሚጠብቁ፥**
**ጽድቅንም ሁልጊዜ የሚያደርጉ ምስጉኖች ናቸው።**

**106:1-3** ይህ የመጀመሪያ አንጓ ሁለት ጭብጦች አሉት።

1. የያህዌ መግለጫ
   ሀ. እሱ ቸር ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 373 II፣ cf. 2 Chr. 5:13፤ 7:3፤ Ps. 25:8፤ 86:5፤ 100:5፤ 107:1፤ 118:1፣29፤ 145:9)
   ለ. የእርሱ ምሕረት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት [ሄስድ]) እና ልዩ ርዕስ፡ ዘላለም [ኦላም])
2. የእርሱ እውነተኛ ተከታዮች መግለጫ
   ሀ. እነርሱ ብርቱ ድርጊቱን ይናገራሉ
   ለ. እነርሱ ያመሰግኑታል
   ሐ. ፍርድን ይጠብቃሉ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፈራጅ፣ ፍትሕ፣ እና ፍርድ)
   መ. እነርሱ (LXX፣ ፔሺታ፣ ቫልጌት፣ ኤምቲ፣ ተመልከት "እሱ") ጽድቅን ይለማመዳሉ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ)

ይህ ገለጻ ዓይነተኛ ነገር ነው፣ ምክንያቱም የሚከተለው የተደገመው ታሪካዊ ጠቃሽ በመሆኑ፣ ለእስራኤል ታማኝ ያለመሆን።

**106፡1** *መዝሙሩ የሚጀምረውና የሚጨርሰው ምስጋናን በማዘዝ ነው።*

1. አመስግኑ – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ *ፒል ተተኳሪ*፣ መዝ. 106:1፣ ዝከ. 107:1፤ 118:1፣29፤ 136:1
2. ምስጋናን ስጡ (አመስግኑ) – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ መዝ. 106:1፣ 1 ዜና. 16:41
3. አመስግኑ – ከቁ 1 ጋር ተመሳሳይ፣ መዝ. 106:48

ታማኝ ተከታዮች ያመሰግኑታል፣ ስለ እርሱ በሚናገሩትና እንደ እርሱ በሚኖሩት! እግዚአብሔርን የሚታዘዝ ሰው ምስጉን ነው (መዝሙር 1)።

**106፡2 *"ኃይል ሥራ"*** ይህ የያህዌን የማዳንና የደጋፊነት ድርጊቶች ያመለክታል። ይህ ጭብጥ ከመዝሙር 105 የቀጠለ ነው (ሙሉውን ማስታወሻ ተመልከት፣ ሰባት ጊዜ የሚከሰትበትን፣ መዝሙር 105 ላይ 105፡1-7 ማስታወሻዎች)።

1. *ኃይል ሥራዎች*፣ መዝ. 106:2 – ቢዲቢ 150፣ ዘዳ. 3:24፤ መዝ. 20:6፤ 71:16፤ 145:4፣12፤ 150:2፤ ኢሳ. 63:15
2. *ተአምራት*፣ መዝ. 106:7 – ቢዲቢ 810 (ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 105:1-7 ላይ)
3. *ሥራዎች*፣ መዝ. 106:13 – ቢዲቢ 795፣ ኢያ. 24:31፤ መዝ. 33:4፤ 93:5
4. *ታላቅ ነገሮች*፣ መዝ. 106:21 – ቢዲቢ 152፣ ማለትም፣ በተለይ ግብፅ ላይ፣ ዘዳ. 10:21፤ እዚህ፤ ግን ደግሞ ሌሎች የያህዌ ድርጊቶች ኢዮብ 5:9፤ 9:10፤ 37:5፤ መዝ. 71:19፤ 126:2 ላይ
5. ድንቆች፣ መዝ. 106:22 – እንደ ቁ. 2 ተመሳሳይ
6. ድንቆች ("አስደናቂ ነገሮች")፣ መዝ. 106:22 – ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ *ኒፋል* አንቀጽ፣ ዘዳ. 10:21፤ 2 ሳሙ. 7:23፤ 1 ዜና. 17:21፤ መዝ. 66:3፤ 145:6፤ ኢሳ. 64:3

**106፡3 "ሁልጊዜ"** ይህ ዓይነተኛ ገጽታ ነው፣ ለደቀ-መዛሙርትነት። እግዚአብሔርን የመሰለ አኗኗር የሙሉ ጊዜ ተግባር ነው! እንግዲህ፣ ይሄንን አስታውሱ፣ በብኪ መቼት። እሱም "ሁለቱን መንገዶች" ያንጸባርቃል፣ የዘዳ. 30፡15፣19፤ መዝሙር 1ን። ገላ. 3፡10-12 ላይ የተጠቀሰው ማሳያ የብኪን ኪዳን ተግባር-ተኮርነት ነው። ምንም እንኳ የአኪ አማኞች በብኪ ሥር ባይሆኑም (ሐዋ. 15)፣ አንድ ጊዜ እግዚአብሔርን በክርስቶስ ካወቅን፣ "ሁልጊዜ" ለእርሱ እንኖራለን። ይሄንን የምናደርገው ተቀባይነትን እንድናገኝ አይደለም፣ ነገር ግን ተቀባይነትን ስላገኘን እንጂ ነው! የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ግብ አንድ ቀን ገነትን ማግኘት አይደለም፣ ነገር ግን በየቀኑ ክርስቶስን መምሰል እንጂ (ሮሜ. 8:28-29፤ 2 ቆሮ. 3:18፤ 7:1፤ ገላ. 4:19፤ ኤፌ. 1:4፤ 2:10፤ 4:13፤ 1 ተሰ. 3:13፤ 4:3፣7፤ 5:23፤ 1ጴጥ. 1:15)!

**መዝሙር ፡ 106፡4-5**

> [4]**አቤቱ፥ በሕዝብህ ሞገስ አስበን፥**
> **በመድኃኒትህም ጐብኘን**
> [5]**የመረጥሃቸውን በጎነት እናይ ዘንድ፥**
> **በሕዝብህም ደስታ ደስ ይለን ዘንድ፥**
> **ከርስትህም ጋር እንጓደድ ዘንድ።**

**106፡4-5** ይህ አንጓ የሚጀምረው በሁለት ተተኳሪዎች ነው፣ እንደ ጸሎት ጥቅም ላይ በዋሉ።

1. አስበኝ – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. ጎብኘኝ ("ዕርዳ") – ቢዲቢ 823፣ ኬቢ 955፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. LXX፣ ፔሺታ፣ እና ቫልጌት "እኛን" የሚል አላቸው በ"እኔን" ምትክ።

እነዚህ ቁጥሮች በስደት ያለ ሰውን የሚያንጸባርቁ ይመስላል (መዝ. 106፡47፣ ማለትም፣ በኪዳኑ ሕዝቦች ኃጢአት ሁሉ ሳቢያ፣ 106፡6)፣ እነርሱም ረዥም ጊዜ ለመኖር የሚጸልዩ፣ ያህዌ ሕዝቡን ሲመልስ እንዲያዩ። እሱ በርካታ ሐረጎችን ይጠቅሳል፣ ወደ ያህዌ የምሕረት ኪዳን የሚያመለክቱ (ማለትም፣ አስብ)።

1. በሞገስህ – መዝ. 106:4
2. የመረጥካቸውን – መዝ. 106:5
3. ሕዝብህን – መዝ. 106:5
4. ርስትህን – መዝ. 106:5

**106:5** ሦስቱን ያልተወሰኑ አወቃቀሮች ተመልከት

1. አይ ዘንድ – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ *ቃል*
2. እደሰት ዘንድ – ቢዲቢ 970፣ ኬቢ 1333፤ *ቃል*
3. እጓደድ ዘንድ – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ *Hithpael*

ሦስቱም ሁሉ የተጠቃለለ (የወል) አትኩሮት እንዳላቸው ተገንዘብ።

1. የመረጥካቸውን
2. ሕዝብህን
3. ርስትህን

ከደኅንነት ጋር በተያያዘ ከማያካትት፣ ግለሰባዊ አጽንዖት ተጠበቁ። የዳንነው የእግዚአብሔርን ቤተሰብ/ የክርስቶስን አካል ለማገልገል ነው። በግለሰቦች ላይ እጅግ የበዛ አትኩሮት፣ ለዔድን ኃጢአት መንፈሳዊ በር ይከፍታል (ዘፍጥረት 3)።

◘ **"ሕዝብህ"** የዕብራይስጡ ቃል "ሕዝብ" ብሎ የተተረጎመው (ቢዲቢ 156) ዘወትር አሉታዊ ቃል ነው፣ አሕዛብን የሚጠቅስ (ማለትም፣ መዝ. 2:1፣8፤ 9:5፣15፣17፣19፣20) ነገር ግን ለእስራኤልም ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል፣ እንደዚህ (ዘፍ. 12:2፤ ዘዳ. 4:6-8፤ መዝ. 33:12፤ ኢሳ. 26:2፤ ኤር. 31:36)።

**መዝሙር ፡ 106፡6-12**

**[6]ከአባቶቻችን ጋር ኃጢአትን ሠራን፥**
**ዐመፅንም፥ በደልንም።**
**[7]አባቶቻችን በግብጽ ሳሉ ተኣምራትህን አላስተዋሉም፥**
**የምሕረትህንም ብዛት አላሰቡም**
**በኤርትራ ባሕር ባለፉ ጊዜ ዐመፁብህ።**
**[8]ኃይሉን ግን ለማስታወቅ።**
**ስለ ስሙ አዳናቸው።**
**[9]የኤርትራንም ባሕር ገሥጸ እርሱም ደረቀ**
**እንደ ምድረ በዳ በጥልቅ መራቸው።**
**[10]ከሚጠሉአቸውም እጅ አዳናቸው፥**
**ከጠላትም እጅ ተቤዣቸው።**
**[11]ያሳደዱአቸውንም ውኃ ደፈናቸው፥**
**ከእነርሱም አንድ አልቀረም።**
**[12]በዚያን ጊዜ በቃሉ አመኑ፥**
**ምስጋናውንም ዘመሩ።**

**106፡6-12** ይህ አንጓ የሚያተኩረው ዘጸአት ላይ ነው።

1. የወቅቱ የእግዚአብሔር ሕዝቦች (መዝ. 106፡6)
   ሀ. እነርሱም እንደ አባቶቻቸው ኃጢአት ሠሩ (የተጠናቀቀ)
   ለ. በደልን ፈጸሙ (የተጠናቀቀ)
   ሐ. ክፋትን ተሞሉ (የተጠናቀቀ)
2. አባቶቻችን (መዝ. 106:7፣ ሌዋ. 26:40፤ ነህ. 9:32-34፤ ኤር. 3:25፤ ዳን. 9:8፣16)
   ሀ. የአንተን ተአምራት መረዳት አልቻሉም
   ለ. የበዛ ቸርነትህንም አላስታወሱም (መሳ. 8:34፤ ነህ. 9:17፤ መዝ. 78:42)
   ሐ. በባሕር ላይ ዓመጹብህ
3. የሆነ ሆኖ ያህዌ አሁንም አደረገ (መዝ. 106፡8-11) በእነርሱ አኳያ
   ሀ. አዳናቸው
   ለ. ኃይሉ እንዲታወቅ አደረገ (ማለትም፣ በድርጊቶቹ ባሕርዩን ገለጠ፣ መዝ. 98:2፤ 103:7)
   ሐ. የኤርትራን ባሕር ገሥጸ (ስለዚህ ሁለንተናዊ ግሥ መዝ. 104፡7ን ተመልከት)
   መ. በዚያ ውስጥ መራቸው
   ሠ. አዳናቸው
   ረ. ዋጃቸው
4. ከያህዌ ድርጊቶች ሁሉ በኋላ አመኑ (ዘጸ. 14፡31፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ) እናም አመሰገኑት (መዝ. 106፡12)

አንዳንድ ሊቃውንት ይሄንን ቁጥር የሚመለከቱት እንደ ብሔራዊ የኃጢአት ኑዛዜ ነው፣ በበዓል ቀን በቤተ-መቅደስ። የይቅርታ ልመናው ያለው መዝ. 106፡47 ላይ ሲሆን በያህዌ ጸጋ መተማመኑ ደግሞ መዝ. 106፡48 ላይ ነው።

**106፡7 "በባሕር"** ኤምቲ ላይ መደጋገም ያለ ይመስላል። ብዙዎቹ ዘመናዊ ትርጉሞች (አየተመት፣ አኢመቅ፣ አአመቅ) "በባሕር" ከሚለው ላይ ተናባቢዎቹን ወስደው ከያህዌ ስም ጋር ያደባልቋቸዋል (መዝ. 78፡17፣56፤ ዳን. 7፡18፣22፣25) ለእግዚአብሔር አንድ መጠሪያ ለማግኘት።

1. ልዑሉ – አየተመቅ፣ አኢመቅ፣ አአመጽ
2. ልዑል – አእቅ

▣ **"ቀይ በባሕር"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቀይ ባሕር

**106፡8** ይህ ቁጥር የሚያተኩረው በትልቁ የያህዌ የማዳን ዓላማ ላይ ነው፣ ዘጸአት ላይ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)። እሱም አሕዛብ እንዲሆኑ ይፈልጋል

1. እስራኤልን እንዲፈሩ
2. እሱን እንዲያውቁ

ችግሩ እስራኤል ኪዳኑን ሙሉ ለሙሉ ፈጽሞ አለመጠበቁ ነው (መዝ. 106፡6-7)። አሕዛብ የተቀበሉት የተዛባ መገለጥ ነው (ሕዝ. 36፡22-23)፣ ስለዚህ ያህዌ አዲስ መንገድ ማዳበር አስፈለገው (ማለትም፣ አዲስ ኪዳን፣ ኤር. 31፡32-34) እነርሱን ለመድረስ። ራሱን ገለጠ (ሕዝ. 36፡23-32)።

**106፡10 "የተዋጀ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መቤዠት/መዋጀት።

**መዝሙር ፡ 106፡13-15**

**[13]ፈጥነውም ሥራውን ረሱ፥**
**በምክሩም አልታገሡም።**

[14]በምድረ በዳም ምኞትን ተመኙ፥
በበረሃም እግዚአብሔርን ተፈታተኑት።
[15]የለመኑትንም ሰጣቸው
ለነፍሳቸው ግን ክሳትን ላከ።

**106፥13-15** ይህ አንጓ ከሥነ-መለኮት አኳያ ከፊተኛው ጋር ተሳስሯል (መዝ. 106፥6-12)። የእስራኤል ንስሐ መግባት፣ መናዘዝ፣ እና ማመን አላበቃም።

የመዝ. 106፥6-12 መዋቅራዊ ገጽታ ተደግሟል።

1. የእነርሱ ድርጊቶች፣ መዝ. 106፥13-14
   ሀ. ፈጥነው ረሱ (ዘወትር ማስጠንቀቂያ፣ ዘዳ. 4:9፤ 6:12፤ 8:14፤ መዝ. 103:2) ቃሉን (መዝ. 106:24)
   ለ. በምክሩም አልታገሡም
   ሐ. በጽኑ ተመኙ (ዘኍ. 11፥4)
2. የያህዌ ምላሽ
   ሀ. ክፉ መሻታቸውን ሰጣቸው (ማለትም፣ ምግብ፣ ዘኍ. 11:4-6፣31፤ መዝ. 78:29-31፤ ደግሞም ሮሜ. 1:24፣26፣28 እይ)
   ለ. ክፉ ሕመም ላከባቸው (ዘኍ. 11፥33፤ የተሻለ አጭር ማብራሪያ ተመልከት፣ በግሌሰን አርከር፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ጠጣር ነገሮች ኢንሳይክሎፔዲያ*፣ ገጽ 136)

**106፥14 "እግዚአብሔርንም በምድረ-በዳ ተፈታተኑት"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 650፣ ኬቢ 702፣ ፒኤል lMየተጠናቀቀ ከዋው ጋር) የእስራኤልን አለማመን ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል፣ በዘጸአትና በመንከራተት ጊዜ (ማለትም፣ በምድረ-በዳ)። ይህም አለማመን የያህዌን የአመራር ቡድን በማጥቃታቸው ይገለጻል (ማለትም፣ ሙሴ እና አሮን፣ ዘጸ. 5:21፤ 14:11፤ 15:24፤ 16:2፤ 17:2፣3፤ 32:1፤ ዘኍ. 11:1፣4፤ 14:1፣2፤ 21:5፤ መዝ. 106:16)። ይኸው ሁነኛ ግሥ ዘጸ. 17:2፣7፤ ዘኍ. 14:22፤ ዘዳ. 6:16፤ 33:8፤ መዝ. 78:18፣41፣56፤ 95:9 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል።

አስገራሚ የሚሆነው ይህ ግሥ ጥቅም ላይ የዋለው እግዚአብሔር ሕዝቡን ሲፈትን ነው (ዘፍ. 22:1፤ ዘጸ. 15:25፤ 16:4፤ 20:20፤ ዘዳ. 8:2፣16፤ 13:3፤ መሳ. 2:22፤ 3:1፣4፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይፈትናል።

## መዝሙር ፡ 106፥16-18

[16]ሙሴንም እግዚአብሔር የቀደሰውንም
አሮንን በሰፈር ተመቀኙአቸው።
[17]ምድርም ተከፈተች ዳታንንም ዋጠችው፥
የአቤሮንንም ወገን ደፈነች
[18]በማኅበራቸውም እሳት ነደደች፥
ነበልባልም ኃጥኣንን አቃጠላቸው።

**106፥16-18** ይህ አንጓ የሚያንጸባርቀው ዘኍልቍ 16ን ነው፣ በምድረ-በዳ የመንከራተት ዘመንን።

**106፥16 "እግዚአብሔር የቀደሰውን"** ይህ የሚጠቅሰው አሮንን ነው፣ ሊቀ-ካህኑን። ዘኍልቍ 16 ላይ ውዝግብ አለ፣ የእስራኤል እውነተኛ መሪ ማን እንደነበረ (ዘኍ. 16፥1-7)። የአሮን የተለየ ቅድስና ከሊቀ-ካህንነት ጋር በተያያዘ በልብሱ ላይ የሚታየው ዘጸአት 28 ላይ ተገልጿል፣ በተለይም ቁጥር 36።

**106፥18 "እሳት"** ዘኍልቁ ላይ በበርካታ ስፍራዎች እሳት ለፍርድ ጥቅም ላይ ውሏል።

1. ናዳብ እና አብዩድ — በእሳት ሞተዋል፣ "ልዩ እሳት" ስላቀረቡ፣ ዘኍ. 3፡4፤ 26፥61
2. የያህዌ እሳት በሚያጕረመርሙ እስራኤላውያን ላይ — ዘኍ. 11፥1-3
3. የቆሬ ዓመጽ — ዘኍ. 16:35፤ 26:10

ዘጸ. 24፥17 እና ዘዳ. 4፡24 ላይ፣ የእግዚአብሔር ክብር እንደሚበላ እሳት ተገልጿል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እሳት)። ይህም የሼኪናህ ክብር ደመናን ይገልጻል፣ እሱም እስራኤላውያንን የሚመራና የሚጠብቅ።

## መዝሙር ፡ 106፥19-27

[19]በኮሬብም ጥጃን ሠሩ፥
ቀልጦ ለተሠራ ምስልም ሰገዱ።
[20]ሣርም በሚበላ በበሬ ምሳሌ
ክብራቸውን ለወጡ።
[21-22]ታላቅ ነገርንም በግብጽ፥
ድንቅንም በካራን ምድር፥
ግሩም ነገርንም በኤርትራ ባሕር ያደረገውን
ያዳናቸውንም እግዚአብሔርን ረሱ።
[23]እንዳያጠፋቸው ቍጣውን ይመልስ ዘንድ
የተመረጠው ሙሴ በመቅሠፍት ጊዜ በፊቱ ባይቆም ኖሮ፥

ያጠፉቸው ዘንድ ተናገረ።
24የተወደደችውን ምድር ናቁ፥
በቃሉም አልታመኑም፥
25በድንኳኖቻቸውም ውስጥ አንጐራጐሩ
የእግዚአብሔርን ቃል አልሰሙም።
26-27በምድረ በዳም ይጥላቸው ዘንድ፥
ዘራቸውንም በአሕዛብ መካከል ይጥል ዘንድ፥
በየአገሩም ይበትናቸው ዘንድ፥
እጁን አነሣባቸው።

**106፡19-27** ይህ አንጓ ዘጸአት 32ንና ዘኍልቍ 14ን ያንጸባርቃል።

**106፡19 "ጥጃ ሠሩ"** ጥጃው እንዲሆን የታሰበው ያህዌ አካላዊ ወኪል ነው (ዘጸ. 32፡8፤ ሁለቱን የወርቅ ጥጃዎች፣ ይሮብአም I በዳን እና ቤቴል ያበጃቸውን እይ)። እሱም የሠራው ከግብፃውያን ለእስራኤላውያን ከተሰጠ ወርቅ ነው። ነገር ግን፣ እሱ ደግሞ እስራኤላውያንን የግብፃውያንን የመራባት ጣዖት የሚያስታውስ ነው (ዘጸ. 32፡6፣19)።

ደግሞም ጥጃ ለከነአናውያን የመራባት አምልኮ ተምሳሌትነት ጥቅም ላይ ይውላል፣ ለኤል እና *በአል* (ማለትም፣ የራስ ሻምራ ጽሑፎች)።

▣ **"ኮሬብ"** ይህ የዕብራይስጥ *ሥር* (ቢ.ዲ.ቢ. 352፣ ኬ.ቢ. 349) ፍችው "መባከን" ወይም "በረሀ" ማለት ነው። ይህ ቃል ተዘውትሮ ጥቅም ላይ ይውላል፣ ዘዳግም ላይ፣ "ያህዌ እስራኤልን ለተገናኘበት ተራራ።" ዘጸአት እና ዘኍልቁ ላይ እሱ "ሲና" ተብሎ ተጠርቷል (ቢ.ዲ.ቢ. 696)፣ ይኸውም ዕብራይስጥ ያልሆነ ቃል። እሱም ከ "ኃጢአት ምድረ-በዳ" ጋር ሊዛመድ ይችላል (ቢ.ዲ.ቢ. 95፣ ዘጸ. 16:1፤ 17:1፤ ዘኍ. 233:11፣12)። ቃሉ ዘወትር ከአነስተኛ የበረሀ ቍጥቋጦ ጋር ይዛመዳል።

ልዩ ርዕስ፡ የሲና ተራራ ስፍራ

**106፡20** እንዴት የሚያስደነግጥ ቁጥር ነው! የእግዚአብሔር የራሱ ሕዝቦች ከአንዱ እውነተኛ አምላክ ወደ ጣዖት ዞሩ (ኤር. 2፡11-13፤ ሰዎች ሁሉ እንደሚያደርጉት፣ ሮሜ. 1፡21-23)!

**106፡22 "በካም ምድር"** ካም (ቢ.ዲ.ቢ. 325 I) ከኖኅ ልጆች አንደኛው ነው። እሱም የበርካታ ሕዝቦች አባት ነበር (ዘፍጥረት 10)።

1. ግብፅ (ምስር)፣ መዝ. 78:51፤ 105:23፣27
2. ከነአን

**106፡23** ያህዌ ለሙሴ ገልጾለታል፣ እነርሱን እንደሚያጠፋቸውና ከእርሱ ጋር እንደሚጀምር፣ ከአብርሃም ጋር እንዳደረገ ሁሉ (ዘጸ. 32፡10)።

ሙሴ ያህዌን ማለደ፣ በእስራኤል በኩል (ዘጸ. 32፡11-13)። ይህም ሙሴን ለማጠንከር ፈተና ይመስለኛል። ያህዌ ሐሳቡን ቀየረ (ዘጸ. 32፡14) ብሎም ለሙሴ ጸሎት ምላሽ ሰጠ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የምልጃ ጸሎት።

**106፡24** በርካታ ጊዜ እስራኤል ያህዌን ለማመን እምቢ ብሏል፣ የከነአንን ምድር እንደሚሰጣቸው (ዘኍ.14:1-3፣31፤ 20:3-4፤ ዘዳ. 9:23፤ ሕዝ. 20:5-8)።

▣ **"ማለላቸው"** *ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 669፣ ኬ.ቢ. 724፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ ከ*ዋው* ጋር) ጥሬ ትርጕሙ "ወደ ላይ ማንሣት" ነው (ማለትም፣ እጅን መሐላ ለመፈጸም ማንሣት)፣ ለያህዌ ተስፋ ዘፍ. 15:18 ላይ። ይህም ዘጸ. 6:8፤ ዘኍ. 14:30፤ ነህ. 9:15 ላይ ተጠቅሷል።

**106:27 *ሁለቱ ግሦች ስደትን ያመለክታሉ።***

1. መጣል ("እንዲወድቅ ማድረግ") – ቢ.ዲ.ቢ. 656፣ ኬ.ቢ. 709፣ *ሂፊል* ያልተወሰነ አወቃቀር፣ መዝ. 106:26ለ
2. መበተን – ቢ.ዲ.ቢ. 279፣ ኬ.ቢ. 280፣ *ፒል* ያልተወሰነ አወቃቀር

ይህ ቀደም ሲል የነበረ ማስጠንቀቂያ ነው፣ በኪዳን አለመታዘዝ ላይ፣ ሌዋ. 26:33፤ ዘዳ. 4:27፤ 28:64፤ 29:28፤ መዝ. 44:11፤ ሕዝ. 20:23። ያህዌ የከነአንን ነገዶች እንዳስወጣ፣ በኃጢአታቸው ምክንያት (ዘፍ. 15:12-21)፣ አሁንም ማዳላት በሌለበት ፍርድ፣ በእስራኤል ላይ ተመሳሳይ አደረገ! ኃጢአት ውጤት አለው!

ስለ ስደት አንድ ተጨማሪ ሐሳብ። እሱ ጎጂና አሳፋሪ የሆነውን ያህል፣ ያህዌ ስለ ራሱ መልእክትን እንዲያሰራጭ ሁኔታዎችን ያመቻቻል። ችግሩ እስራኤል የተሳሳተውን መልእክት መስጠት መቀጠሉ ነው (ሕዝ. 36፡22-23)።

"አዲስ ኪዳን" የኤር. 31፡31-34 የሚያተኩረው በያህዌ የራሱ መገለጥ ላይ ነው፣ በቸርነታዊ ድርጊቶቹ፣ ለዓመጸኛው እስራኤል (ሕዝ. 36፡24-38)።

## *መዝሙር* ፡ 106፡28-31

28በብዔል ፌጎርም ተባበሩበት፥
የሙታንንም መሥዋዕት በሉ።
29በሥራቸውም አስመረሩት፥
ቸነፈርም በላያቸው በዛ።

[30]**ፊንሐስም ተነሥቶ ፈረደባቸው፥**
**ቸነፈሩም ተወ**
[31]**ያም እስከ ዘላለም ለልጅ ልጅ**
**ጽድቅ ሆኖ ተቈጠረለት።**

**106፡28-31** ይህ አንጓ ከዘኍልቍ 25 ጋር ይዛመዳል። እስራኤል በሞአብ የመራባት አምልኮ ውስጥ ገብቷል። አመንዝራነት ዋነኛው ችግር ነበር፣ በእስራኤል ታሪክ። ማስታወሻዬን አኪያለሁ፣ ከዘዳ. 18፡10-11። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) የመራባት አምልኮ።

**ዘዳ. 18፡10-11** ተለጣጣቂ አንቀጾች አሉ፣ የከነአንን አመንዝራነት የሚገልጹ፡

1. አአመመቅ፣ አአመመቅ፣ "ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን በእሳት ውስጥ የሚያሳልፍ" – ቢዲቢ 716፣ ኬቢ 778፣ *ሂፊል* አንቀጽ
2. አአመመቅ፣ "መናፍስት ጠሪውን" – ቢዲቢ 890፣ ኬቢ 1115፣ *ቃል* አንቀጽ (ሁለቱንም ግሥ እና ስም ይጠቀማል)
   አኪጀት፣ አእት፣ "ጥንቆላን የሚያደርግ"
   አየተመቅ፣ አኢመቅ፣ አኢቅ፣ "መናፍስት ጠሪውን"
   ጀፒኤስአኤ፣ "ሐሰተኛ ነቢይ"
3. አአመመቅ፣ "ጥንቆላን የሚለማመድ" – ቢዲቢ 778 II ኬቢ 857፣ *ፖል* አንቀጽ
   አኪጀት፣ አየተመቅ፣ አኢመቅ፣ ጀፒኤስአኤ፣ "የሚያሟርት"
   አኢቅ፣ "ሟርተኛ"
   አኢት፣ "ሞራ ገላጭ"
4. አአመመቅ፣ አኪጀት፣ NIV፣ "አስማት የሚተረጉም" – ቢዲቢ 638 II፣ ኬቢ 690፣ ፒል አንቀጽ
   አየተመቅ፣ አኢመቅ፣ "ሐሰተኛ ነቢይ"
   ጀፒኤስአኤ፣ "መናፍስት ጠሪ"
   አእት፣ "የሚያሟርት"
5. አአመመቅ፣ አኪጀት፣ አየተመቅ፣ አኢመቅ፣ ጀፒኤስአኤ፣ አእት፣ "ሟርተኛ" – ቢዲቢ 506፣ ኬቢ 503፣ ፒል አንቀጽ
   አኢቅ፣ "ጠንቋይ"
6. አአመመቅ፣ "መጽሐፍ ገላጭ (ደብተራ)" – ቢዲቢ 287፣ ኬቢ 287፣ *ቃል* አንቀጽ (ግሥ እና ስምን ይጠቀማል)
   አኪጀት፣ "መጽሐፍ ገላጭ"
   አየተመቅ፣ ጀፒኤስአኤ፣ አኢቅ፣ አእት፣ "መጽሐፍ ገላጭ"
   አኢመቅ፣ "መጽሐፍ የሚገልጥ"
7. አአመመቅ፣ አኪጀት፣ "የሚጠይቅ" (ማለትም፣ መካከለኛ) – ቢዲቢ 981፣ ኬቢ 1371፣ *ቃል* አንቀጽ
   አየተመቅ፣ ጀፒኤስአኤ፣ "መናፍስት ጠሪ"
   አኢመቅ፣ "መናፍስት ጠሪ"
   አኢቅ፣ "መካከለኛ"
   አእት፣ "መናፍስትን የሚጠይቅ"
8. አአመመቅ፣ አኪጀት፣ አኢቅ፣ "የሚጠይቅ" [ተብሎ የሚገመት] (ማለትም፣ መናፍስት) – ቢዲቢ 981፣ ኬቢ 1371፣ *ቃል* አንቀጽ (ተብሎ የሚገመት)
   አየተመቅ፣ "መናፍስት ጠሪ"
   አኢመቅ፣ "መካከለኛ"
   ጀፒኤስአኤ፣ "ክፉ መናፍስት"
   አእት፣ "ጥንቆላን የሚለማመድ"
9. አአመመቅ፣ አኪጀት፣ "ሙታንን የሚጠራ"
   ሀ. ቢዲቢ 205፣ ኬቢ 233፣ *ቃል* አንቀጽ
   ለ. ቢዲቢ 559፣ ኬቢ 562፣ *ቃል* አንቀጽ
   አየተመቅ፣ "ከሙታን ንግግሮችን የሚሻ"
   አኢመቅ፣ አእት፣ "ጠንቋይ"
   ጀፒኤስአኤ፣ "ሙታንን የሚጠራ"
   አኢቅ፣ "ሙታንን የሚጠራ"

ከተለያዩ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ማየት እንደምትችሉት፣ እነዚህ ቃላት አንዳንድ ንብብሮሽ አሏቸው። እነዚህ ቃላት የተለያዩ ዓይነቶች የጣዖት አምልኮ ልምምዶችን የሚጠቅሱ ይመስላሉ፣ ነገር ግን የእነርሱ ርግጠኛ ፍች ግልጽ አይደለም፣ ለዘመናዊዎቹ የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች። አጭር ማብራሪያ ተመልከት (1) የመጽሐፍ ቅዱስ ምናባዊነት ምስያ መዝገበ-ቃላት፣ ገጽ 524-528 እና 608-610 እና ደግሞ (2) የብሉይ ኪዳን ተመሳስሎ በሮበርት ቢ. ጊርድልስቶን፣ ገጽ 296-302። አጠቃላይ ስዕሉ የወደፊቱን ለማወቅና ለመጠቀም መሞከር ነው፣ ለግላዊ ጠቀሜታ። የያህዌ ሕዝቦች እሱን እንዲያመሰግኑትና እንዲያገለግሉት ይገባል። አሮጌው ዋነኛ ኃጢአት፣ "እኔ ልቅደም" የሰው ልጅ ችግሮች ሁሉ ሥር ነው!

**18፡10 "ወንድ ልጁን ወይም ሴት ልጁን በእሳት የሚያሳልፍ"** ይህ የመራባት ጣዖትን፣ ሞሎክን የማምለክ ጠቃሽ ነው። በእስራኤል የበኵር ልጅ (ዘጸአት 13) ለያህዌ ይሰጥ ነበር፣ እሱን ለማገልገል። በከነአን የበኵር ልጅ ለሞሎክ በእሳት መሥዋዕትነት ይቀርባል፣ መራባትን ለማረጋገጥ፣ (ዘዳ. 12:31፤ ሌዋ. 18:21)። እንዲያውም በ2 ነገሥ. 21፡6 ላይ አንድ የሚጠቀስ አለ፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ ይሄንን ሐሰተኛ አማልክት ለማምለኩ! እሱም ደግሞ መጻዒውን ከማወቅ ጋር ሊዛመድ ይችላል (2 ነገሥ. 3፡26፡27)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሞሎክ።

◘ **"መናፍስት ጠሪነት"** ይህ ከዕብራይስጥ ሥር "መለኮት" ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 890፣ ዘኍ. 22:7፤ 23:23፤ ሕዝ. 21:21፤ 2 ነገ. 17:17)። እሱም አጠቃላይ ቃል ነው፣ በርካታ የተለያዩ ዘዴዎችን የሚገልጽ፣ ነገር ግን የሁሉም ሐሳብ የመለኮትን ፍቃድ መወሰን ነው፣ በድርጊታዊ ወይም ተፈጥሯዊ ዘዴዎች፣ ማለትም የበጎችን ጉበት መመርመር ወይም ቀስት መጣል። እሱም የተመሠረተው በአምልኮተ-ባዕድ አመለካከት ሲሆን፣ ይኸውም መጻዒው መረጃ የተሸሸገው በተፈጥሯዊ ሁነቶች ውስጥ ሲሆን፣ ተሰጥዖ ያላቸው ሰዎች (ማለትም፣ ሐሰተኛ ነቢያት፣ ለምሳሌ፣ ኤር. 27:9፤ 29:8፤ ሕዝ. 13:9፤ 22:28) ያውቁታል፣ በዚህ መጻዒ ላይ ተጽዕኖ ያሳርፋሉ።

◘ **"ጥንቆላን የሚለማመድ"** ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 778 II፣ ኬቢ. 857) "ደመና" ከሚለው ቃል ጋር ይዛመዳል (ቢ.ዲ.ቢ. 777)። የሥነ-ቋንቋ ሊቃውንት የሚያስቡት ቃሉ ከድምጽ ጋር እንደሚዛመድ ነው፡

1. የነፍሳት ጢዝታ
2. የነፋስ ድምጽ በዛፎች መካከል
3. ያልታወቀ አፈ-ታሪክ (ደመና ከሆነ፣ ከዚያም ከዕይታ ጋር ይዛመዳል)

ከሙሴ ጽሑፎች ትይዩው ምንባብ፣ ይሄንን የጣዖት አምልኮ ልምምድ የሚከለክለው ሌዋ. 19:26-20:8 ነው (በተለይ. 19:26 ተመልከት)። ይኸው ተመሳሳይ ቃል ደግሞ መሳ. 9:37፤ 2 ነገ. 21:6፤ 2 ዜና. 33:6፤ ኢሳ. 2:6፤ 57:3፤ ኤር. 27:9፤ ሚክያስ 5:12 ላይ ይገኛል።

◘ **"ሞራ ገላጭ"** የዚህ ቃል ፍች (ቢ.ዲ.ቢ. 638 II፣ ኬቢ. 690) ርግጠኝነት የለውም። በሶርያንኛ ፍችው "ግልጽ ያልሆነ የድጋም ቃል ማነብነብ" ነው (ኬቢ. 690)። ሥሩ በርካታ አጠቃቀሞች አሉት፡

1. እባብ – ቢ.ዲ.ቢ. 638 I
2. ግሥ በፒይል ያለ ብቻ፣ (ቢ.ዲ.ቢ. 638 II) ፍችውም፡
   ሀ. መናፍስት ጠሪነትን መለማመድ
   ለ. ምልክቶች/ሞራን መቃኘት
3. መዳብ - ነሐስ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 638 III
4. ያልታወቀ - ቢ.ዲ.ቢ. 638 IV

◘ **"አስማተኛ"** ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 506፣ ኬቢ. 503) መሠረታዊ ፍችው "መቆራረጥ" ነው (1) ውሕዶችን እንደ ማድቀቅ፣ ለአስማታዊ መጠጥ ወይም (2) አንዱን መቆራረጥ፣ የመለኮትን ትኩረት መሳቢያ መንገድ (ማለትም፣ የሶርያኛ አጠቃቀም፣ 1 ነገ. 18:28)። ይህ ቃል የፈርዖንን ጠቢባን ሰዎች ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል ዘጸ. 7:11 ላይ እና የናቡከደነፆር ጠቢባን ሰዎች ዳን. 2:2 ላይ።

**18:11 "የጽሑፍ አስማት የሚደግም"** ይህ በጥሬው "ገመድ መተብተብ፣" "ከ...ጋር መተባበር፣" ወይም "አንድ ላይ መሆን" ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 287፣ ኬቢ. 287)። መዝሙር 58:5 እና መክ. 10:11 ላይ እሱ የሚያመለክተው የእባብን አስማት ነው። መጠነኛ ልዩነት ባለው አነባበብ የባቢሎናውያንን ሐሰተኛ ጠቢባን ሰዎችን ይገልጻል፣ ኢሳ. 47:8-11 ላይ።

◘ **"ሟርተኛ"** የአንቀጹ (ቢ.ዲ.ቢ. 981፣ ኬቢ. 1371) መሠረታዊ ፍች "መጠየቅ" ወይም "ጥያቄ ማቅረብ" ነው። እዚህ መንፈሳዊውን ግዛት መጠየቅ ማለት ነው (ምሳ፣ ያህዌ፣ ኢያ. 9:14 ወይም ጣዖታት ሆሴዕ 4:12)።

የመጀመሪያው ስም "ሟርተኛ" (ቢ.ዲ.ቢ. 15) ለመግለጽ አስቸጋሪ ቃል ነው። አንዳንዶች ቃሉን የሚመለከቱት ሌዋ. 19:31፤ 20:6፣27 ላይ ጥቅም ላይ እንደዋለ ነው፣ እንደ (1) ጉድጓድ ወይም መቃብር መናፍስት ንግርት የሚያደርጉበት፣ (2) የ "አባት" ዓይነት፣ እሱም የዘር ግንዶች አምልኮ የሚካሄድበት። እሱም LXX ላይ በኢሳ. 8:19 እንደ "አንጎራጓሪ ሰው" ተተርጉሟል። በዚህ ምክንያትና በኢሳ. 29:4 አንዳንዶች የሚያስቡት፣ ፍችው "የጩኸት ድምጽ ማሰማት" ወይም "ማንሾካሾክ" ነው። ይኸውም "በተለያዩ ድምጾች መናገር" የሚል አንድምታ ያመጣል። ሆኖም፣ ከ1 ሳሙ. 28:7-9 አኳያ እሱ ሊዛመድ የሚችለው በምድር ውስጥ ካለ ሰው ጋር የመነጋገር ችሎታ ያለው ወይም ከሙታን ጋር ወይም በመቃብር ካሉ መናፍስት ጋር ተግባቦት ማድረግ የሚችል ነው፣ ማለትም፣ መናፍስት ጠሪ።

ሁለተኛው ስም፣ "መናፍስት" (ቢ.ዲ.ቢ. 396) የዕብራይስጥ ቃል "ማወቅ" ዓይነት ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 395)። እሱም የሚያመለክተው የመንፈሳዊውን ዓለም እውቀት ላለው ሰው ነው ወይም በመንፈሳዊ ዓለም ከሚኖሩት ጋር የግንኙነት እውቀት ያለው ነው (ኢሳ. 8:19፤ 19:3)።

◘ **"ሙታንን የሚጠራ"** ይህ ሐረግ የሁለት ቃል አንቀጾች ድብልቅ ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 205፣ ኬቢ. 233፣ "መጠየቅ" እና ቢ.ዲ.ቢ. 559፣ ኬቢ. 562፣ "ሙታንን")። ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ የሚያመለክተው ሞርተኞችንና "መናፍስት ጠሪዎችን" ነው። እነዚህ የተማሩ፣ ተውህቦ (ስጦታ) አላቸው የሚባሉ ሰዎች ሙታንን ይገናኛሉ፣ ስለ መጻዒው መረጃ ለማግኘትና በእሱም የተጽዕኖ ኃይል ለማሳደር።

ሁሉም የጥንት ባህሎች ከሞት በኋላ ባለ ሕይወት ያምናሉ። ለብዙዎች በጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ ይህ ሁለት አማራጮች አሉት፡

1. የዘር-ግንዶች አምልኮ፣ ማለትም የቤተሰብ አባላት መናፍስት በአሁኑና በመጻዒው ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩበት
2. የሥጋዊ ኃይል (ከዋክብት፣ የተፈጥሮ ኃይላት) ወይም የመንፈሳዊ (አጋንንት፣ መናፍስታዊ) ጥቅም ላይ ይውላሉ ግለሰባዊ መዳረሻዎችን ለማወቅና ተጽዕኖ ለማሳረፍ።

**መዝ. 106:28 "የሙታንን መሥዋዕት በሉ"** ኤምቲ "የተሠዋ" የሚል ግሥ የለውም። "ሙታን" (ቢ.ዲ.ቢ. 559፣ ቃል፣ ቁ. 1፣መ) ቃል የድርጊት አንቀጽ ነው፣ እሱም ሕልውና የሌላቸውን የአምልኮተ ባዕድ ጣዖታትን የሚጠቅስ (ዘኍ. 25:2)፣ የሞቱ ሰዎችን ሳይሆን (ዘዳ. 26:14)። አእቅ፣ አኢመቅ፣ እና የተእመቅ እንዲሁ ነው የሚተረጉሙት።

አእቅ — “ሙታን አለቆች”
አኢመቅ — “ሕይወት የሌላቸው አማልክት”
የተእመቅ — “ሕይወት የሌላቸው አማልክት”

**106፡29 “ድርጊታቸውን”** አንዱ ሊደንቀው ይችላል የሆነ ተብሎ ማወዳደሪያ መኖሩ
1. የእስራኤላውያን አመንዝሮች (ጣዖት አምላኪዎች) ድርጊቶች፣ መዝ. 106፡29፣ 39
2. የያህዌ ድርጊቶች፣ መዝ. 106፡2፣7፣13፣21-22

እንዴት ያለው ተቃርኖ ነው!

**106፡31 “ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት”** ይህ ርግጠኛ ሐረግ ነው፣ ለአብርሃም በእምነት መጽደቅ የተነገረለት፣ ዘፍ. 15፡6 ላይ፣ በጳውሎስም ሮሜ. 4፡3፤ ገላ. 3፡6 ላይ የተጠቀሰ። እዚህ ግሡጋ ያለው ብቸኛ ልዩነት (ቢዲቢ 362፣ ኬቢ 359፣ ኒፋል ያልተጠናቀቀ) እና እዚያጋ ያለው (ቃል ያልየተጠናቀቀ) ግሣዊ ገጽታ ነው። ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት ዘፍ. 15፡6 ቀጥታ ድረ-ገጽ መስመር ላይ www.freebiblecommentary.org.

የፊንሐስ ካህኑ ድርጊት ዘኁ. 25፡11-13 ላይ ተገልጿል። የእርሱ ድርጊት፣ እንደ አብርሃም፣ በያህዌ ላይ ያለውን እምነት ያሳያል።

**106፡31** “ለልጅ ልጅ ሁሉ እስከዘላለም” የፊንሐስ ድርጊት የእውነተኛ ታማኝ ተከታይ ምሳሌ ነው። ይህ ምስክርነት የተጠበቀውና በቀጣይነትም የሚናገረው ለእርሱ እምነት/ታማኝነት ነው።

አኗኗራችን በሰዎች ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል፣ ከሞትን ከረጅም ጊዜ በኋላ!

***መዝሙር* ፡ 106፡32-33**

**32-33በክርክር ውኃ ዘንድም አስቈጡት፥**
**መንፈሱን አስመርረዋታልና**
**ስለ እነርሱም ሙሴ ተበሳጨ**
**በከንፈሮቹም በስንፍና ተናገረ።**

**106፡32-33** ይህ አንጓ የዘኍልቁ 20ን ሁነቶች ያንጸባርቃል። እስራኤላውያን በቃላቸው ሙሴን አበሳጩት፣ በመሪባ፣ እሱም በስንፍና ተናገረ (ዘኁ. 20፡12፤ 27፡14፤ ዘዳ. 1፡37፤ 3፡26-27፤ 34፡4)። እግዚአብሔር ግለሰቦችን የሚያከብር አይደለም፤ አለመታዘዝ ውጤት አለው (ገላ. 6፡7፣ ሙሉውን ማስታወሻ ድረ-ገጽ ላይ ተመልከት)።

**106፡33 “መንፈሱን”** አአመመቅ “መንፈስ” የሚለውን በትልልቁ ፊደላት አስፍሮታል (ቢዲቢ 924)፣ እሱም የያህዌን መንፈስ የሚያመለክት፣ ነገር ግን ዐውደ-ጽሑፉ በግልጽ የሚያመለክተው የሙሴን መንፈስ ነው (ማለትም፣ የሕይወት ኃይል)። መዝ. 106፡33ለ ላይ ትይዩው መስመር፣ “እሱ” የሚያመለክተው ሙሴን ነው።

እሱ ለውይይት ክፍት የሆነ ሐሳብ ነው፣ ምክንያቱም ከሙሴ ጋር የነበረው የእግዚአብሔር በመሆኑ (ዘኁ. 11፡17፤ ነህ. 9፡20)፣ ከእስራኤል (ዘኁ. 24፡3)፣ እና ከሁለቱም (ኢሳ. 63፡10-14)።

***መዝሙር* ፡ 106፡34-39**

**34እግዚአብሔርም እንዳላቸው**
**አሕዛብን አላጠፉም**
**35ከአሕዛብም ጋር ተደባለቁ፥**
**ሥራቸውንም ተማሩ።**
**36ለጣዖቶቻቸውም ተገዙ፥**
**ወጥመድም ሆኑባቸው።**
**37ወንዶች ልጆቻቸውንና ሴቶች ልጆቻቸውን ለአጋንንት ሠው**
**38የወንዶች ልጆቻቸውንና የሴቶች ልጆቻቸን ደም፥**
**ለከነዓን ጣዖቶች የሠውአቸውን**
**ንጹሕ ደም አፈሰሱ፥**
**ምድርም በደም ረከሰች።**
**39በሥራቸው ረከሱ፥**
**በማድረጋቸውም አመነዘሩ።**

**106፡34-39** ይህ አንጓ እግዚአብሔር ለእስራኤል የሰጠውን ቃል ያንጸባርቃል፣ ከከነአናውያን ጋር ስለ መደባለቅ (ዘጸ. 34፡10-17፤ ዘዳ. 7፡1-6፣16፤ 20፡16-18)። መጽሐፈ ኢያሱ የሚገልጸው ያዋነኞቹ የተመሸጉት የከነአን ከተሞችን ሽንፈት ነው፣ ነገር ግን እያንዳንዱ ነገድ ከገዛ ራሱ ነገዳዊ ስፍራ (ርስት) ከነአናውያንን የማስወጣት ሥራ መጨረስ ይኖርበታል። እነርሱ አላደረጉትም (ማለትም፣ መሳ. 1፡21፣27፣ ወዘተ)። ውጤቱም በግልጽ ተቀምጧል፣ ዘኁ. 33፡50-56 ላይ!

**106፡35 “አሕዛብ”** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የፍልስጥኤም ቅድመ-እስራኤላውያን ነዋሪዎች።

**106፡36 "ወጥመድም ሆኑባቸው"** ይህ ቃል፣ "ወጥመድ" (ቢ.ዲ.ቢ. 430)፣ የእንስሳን ወጥመድ የሚጠቅስ ነው ("ማጥመጃ ምግብ" ወይም "የአሳ ማጥመጃ")። እሱም በዘይቤአዊነት የከነአናውያንን የመራባት አምልኮ መፈታተን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ነው (ዘጸ. 23:33፤ ዘዳ. 7:16፤ መሳ. 2:3)።

**106፡37-38** ይህ የሚያመለክተው የመራባትን አምላክ፣ ሞሎክን ማምለክ ነው።

ልዩ ርዕስ፡ ሞሎክ

**106፡37 "አጋንንት"** ይህ (ቢ.ዲ.ቢ. 993) የሚያመለክተው የአምልኮተ-ባዕድን ጣዖታት ነው (ዘዳ. 32:17)። ቃሉ ሁለቴ ብቻ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፣ ብኪ ላይ። እሱም ከአራምኛ የውሰት ቃል ሊሆን ይችላል። የባዕድ አምልኮ ጣዖታት፣ እንደ ኢጋንንት ይታያል፣ ብኪ ላይ 1 ቆሮ. 10:19-20 እና ራዕ. 9:20።

ልዩ ርዕስ፡ መላእክት እና ኢጋንንት

**106፡38 "ምድርም ረከሰች"** የከነአን ምድር በከነአናውያን ረክሳ ነበር (ዘፍ. 15፡16) አሁን ደግሞ በእስራኤላውያን (ዘኍ. 35:33-34፤ ኤር. 3:2-10)። ከነአን የያህዌ ነው። የእርሱ ምድር ነው።

**106፡39** "በማድረጋቸውም አመነዘሩ" ይህ (ቢ.ዲ.ቢ. 275፣ ኬቢ. 275፣ ቃል 1Mየተጠናቀቀ ከዋው ጋር) የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ለአመንዝራዎች አምልኮ (መሳ. 2፡17፤ ሕዝቅኤል 23፤ ሆሴ. 5፡3)። እሱም የተመሠረተው ያህዌን እንደ አባት እና እስራኤልን እንደ ሚስት በሚያመለክት ምስያ (ምናብ) ነው (ሆሴ. 1-3)። ሌላ አማልክትን ተከትሎ መሄድ እንደ "መንፈሳዊ አምንዝራነት" ይታያል (ዘጸ. 34፡15፤ ዘኍ. 15:39፤ መዝ. 73:27፤ ሆሴ. 4:12፤ 9:1)። አንዳንዴ ምስያው ሁለቱንም ዘይቤአዊና በጥሬው ሊሆን ይችላል፣ ምክንያቱም ብዙዎቹ/አብዛኞቹ የመራባት አምልኮዎች በማስመሰል ጥንቆላ ስለነበሩ (ማለትም፣ የግብረ-ሥጋ ግንኙነት በአምልኮ ስም እና በአምልኮ ስፍራ)።

## መዝሙር ፡ 106፡40-43

**40 የእግዚአብሔርም ቍጣ በሕዝቡ ላይ ነደደ፥**
**ርስቱንም ተጸየፈ።**
**41 ወደ አሕዛብም እጅ አሳለፋቸው፥**
**የሚጠሉአቸውም ገዙአቸው።**
**42 ጠላቶቻቸውም ግፍ አደረጉባቸው፥**
**ከእጃቸውም በታች ተዋረዱ።**
**43 ብዙ ጊዜ አዳናቸው**
**ነገር ግን በምክራቸው አስመረሩት፥**
**በኃጢአታቸውም ተዋረዱ።**

**106፡40-43** ይህ የዘጸአት፣ የምድረ-በዳ መዞር፣ የድል፣ የፈራጆች፣ እና የመንግሥት ጊዜያት ማጠቃለያ ነው። ብኪ የእስራኤል ለመታዘዝ አለመቻል የሰፈረበት (የተመዘገበበት) ነው (ገላትያ 3)!

ያህዌ በእስራኤል አመንዝራነት፣ ዓመጻ፣ እና አለማመን የወሰደውን ርምጃ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን ብርቱ ስሜታዊ ቃላት ተገንዘብ።

1. የእግዚአብሔርም ቍጣ በሕዝቡ ላይ ነደደ (ዘዳ. 1:34-35፤ 9:19)
2. ርስቱንም ተጸየፈ (ሌዋ. 26:30፤ ዘዳ. 32:19)
3. አሳልፎም ሰጣቸው. . . (ማለትም፣ የዕብራይስጥ ፈሊጥ፣ ለመናቅ)፣ በተለያዩ ግን ትይዩ ሐረጋት ይቀጥላል፣ መዝ. 106:41-42 ላይ

**106:42 "እነርሱም ተዋረዱ"** ኤቢ. (ገጽ. 75) ይገልጻል "የከነአን" ተናባቢዎች (ቢ.ዲ.ቢ. 488) ከዚህ ግሥ ጋር ተመሳሳይ መሆናቸውን (ቢ.ዲ.ቢ 488፣ ኬቢ 484፣ ኒፋል ያልተጠናቀቀ ከዋው ጋር)። ይህ ሆን ተብሎ የተደረገ የድምጽ ተመሳስሎ (ጨዋታ) ይሆናል። የከነአን ነገዶች የያህዌን እምነተ-ቢስ ነገዶች አዋረዱ።

## መዝሙር ፡ 106፡44-46

**44 እርሱ ግን ጩኸታቸውን በሰማ ጊዜ**
**ጭንቃቸውን ተመለከተ**
**45 ለእነርሱም ኪዳኑን አሰበ፥**
**እንደ ምሕረቱም ብዛት ተጸጸተ።**
**46 በማረኩአቸውም ሁሉ ፊት**
**ሞገስን ሰጣቸው።**

**106፡44-46** ይህ አንዴ የያህዌን ቸርነታዊ ምላሽ ያሳያል፡፡

1. እሱም ጭንቃቸውን ተመለከተ (ዘጸ. 2:25፤ 5:7፤ ነህ. 9:9)
2. ጮኸታቸውን ሰማ (ዘጸ. 2:23-25፤ 3:7-9፤ ዘኍ. 20:16፤ መሳ. 3:9፤ 6:7፤ 10:10፤ ነህ. 9:27)
3. ኪዳኑንም አሰበ (ዘጸ. 2:24፤ ሌዋ. 26:40፣42፣45፤ መዝ. 105:8፣42)

4. እንደ ምሕረቱም ብዛት ተጸጸተ (ሙሉ ማስታወሻውን ድረ-ገጽ ላይ ተመልከት፣ ዘፍ. 6፡6)
5. ርኅራኄ እንዲያገኙ አደረገ (1 ነገ. 8:50፤ 2 ዜና. 30:9፤ ዕዝራ 9:9፤ ነህ. 1:11፤ ኤር. 42:12)
6. መዝ. 106:43ሀ፣ ሌላው የያህዌ ሞገሳዊ ፍላጎት እንደሆነ ተገንዘብ፡፡

**106፡45 "ኪዳን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን

**መዝሙር ፡ 106፡47-48**

**47አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፥ አድነን**
**ቅዱስ ስምህን እናመሰግን ዘንድ፥**
**በምስጋናህም እንመካ ዘንድ፥**
**ከአሕዛብ መካከል ሰብስበን።**
**48ከዘላለም እስከ ዘላለም**
**የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር ይባረክ**
**ሕዝብም ሁሉ አሜን ይበል።**
**ሃሌ ሉያ።**

**106፡47-48** እነዚህ ቃላት ደግሞ 1 ዜና. 16፡35-36 ላይ ይገኛሉ፡፡ ይህ መዝሙር ያህዌን በማመስገን ይጀምራል፣ ለታማኝ ተከታዮቹ ስላለው ጸጋ። እስራኤል ግን የታመነ አልሆነም! አሁን መዝሙረኛው ወደ ያህዌ ይጸልያል፣ በእነርሱ አኳያ እንዲሠራ እና እስራኤልን ከስደት እንዲመልስ!

1. አድነን – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ 1 ዜና. 16:35
2. ከአሕዛብም ሰብስበን – ቢዲቢ 867፣ ኬቢ 1062፣ *ፒል ተተኳሪ*፣ ዘዳ. 30:3፤ መዝ. 147:2፤ ኢሳ. 11:12፤ 56:8፤ ሕዝ. 39:28

የመመለሱ ዓላማ እስራኤል የሚያደርገው

1. ለቅዱሱ ስምህ ምስጋና ያቀርባል – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል ያልተወሰነ አወቃቀር*
2. በምስጋናህ ይባረካል – ቢዲቢ 986፣ ኬቢ 1387፣ *ሂዝፓል ያልተወሰነ አወቃቀር*

**106፡48 "እግዚአብሔር ይባረክ"** ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ *ቃል ተገብሮ አንቀጽ*) መዝ. 41:13፤ 72:18፤ 89:52 ላይ ዳግም ይከሰታል። እስራኤል አምላካቸውን እንዲያመሰግኑ ይገባል፣ ስለ ማንነቱና ለእነርሱ ስላደረገው።

የመለኮትን ኪዳናዊ መጠሪያ ተገንዘብ።

1. አምላካችን እግዚአብሔር ሆይ፣ መዝ. 106፡47
2. የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር፣ መዝ. 106፡48

▣ **"ከዘላለም እስከ ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም ('ኦላም)።

▣ **"ሕዝብም ሁሉ አሜን ይበል"** *አአመመቅ ይሄንን ሐረግ የሚተረጉመው እንደ ተጽዕኖዊ ነው፣ ነገር ግን እሱ ቃል የተጠናቀቀ ነው።*

▣ **"አሜን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሜን። እስራኤል (ማለትም፣ "ሕዝብ") የሚያረጋግጠው የያህዌን ባራኪነት ነው።

▣ **"ሃሉ ሉያ"** ይህ መዝሙር የሚጠናቀቀው እንደ መዝሙር 105 እና 104 ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ነው። ይህ የአምልኮ ሥርዓታዊ ሐረግ ነው፣ የሚከፍት (ማለትም፣ መዝ. 105፡1) እና የሚዘጋ (ማለትም፣ መዝ. 105፡45) ብዙ መዝሙራትን። እሱም የሚያመለክተው በአምልኮ መቼት ላይ መነበባቸውን ነው።

"ጌታ" የ*ያህ* አጽሕሮተ መልክ ነው (ያጠረ) (ቢዲቢ 219)።

በሚያስገርም መልኩ ይህ LXX ላይ አልተገኘም፣ ነገር ግን ፔሺታ ላይ ተካትቷል። በርግጥ ሊሆን የሚችለው መዝ. 106:48ሐ-መ የአምልኮ ሥርዓታዊ መዝጊያ ማገልገሉ ነው፣ ለአራተኛው የመዝሙር መጽሐፍ (ማለትም፣ መዝ. 41:13፤ 89:52)።

# መዝሙር 107
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ ሰዎችን ከብዙ መከራ ያድናቸዋል<br>ኤምቲ መግቢያየለውም | ለጌታ ምስጋና ማቅረብ ስለ ታላቅ የማዳን ሥራው | የአብሮነት ምስጋና ማቅረብ ለመናኞች | ምስጋና ለአምላክ መልካምነት | እግዚአብሔር፣ ለአደጋ ሁሉ መጠጊያ |
| 107:1-3 | 107:1-3 | 107:1-3 | 107:1-3 | 107:1 |
| | | | | 107:2-3 |
| 107:4-9 | 107:4-9 | 107:4-9 | 107:4-9 | 107:4-5 |
| | | | | 107:6-7 |
| | | | | 107:8-9 |
| 107:10-16 | 107:10-16 | 107:10-16 | 107:10-16 | 107:10-12 |
| | | | | 107:13-14 |
| | | | | 107:15-16 |
| 107:17-22 | 107:17-22 | 107:17-22 | 107:17-22 | 107:17-18 |
| | | | | 107:19-20 |
| | | | | 107:21-22 |
| 107:23-32 | 107:23-32 | 107:23-32 | 107:23-32 | 107:23-24 |
| | | | | 107:25-27 |
| | | | | 107:28-30 |
| | | | | 107:31-32 |
| 107:33-38 | 107:33-38 | 107:33-38 | 107:33-38 | 107:33-34 |
| | | | | 107:35-36 |
| | | | | 107:37-38 |
| 107:39-43 | 107:39-43 | 107:39-43 | 107:39-42 | 107:39-40 |
| | | | | 107:41-42 |
| | | | 107:43 | 107:43 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ማስታወሻ)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኀላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ።ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. በመዝሙር 105፣ 106፣ እና 107 መካከል ትስስሮሽ እንዳለ ይታሰባል (ማለትም፣ ተመሳሳይ የመግቢያ ሐረግ)። ምንም እንኳ እነዚህ በመጽሐፍ ምድብ የተከፋፈሉ ቢሆኑም፣ ርዕሰ-ጉዳያቸውና የቃላት አካሄዳቸው አንድ ላይ ያያይዛቸዋል። LXX የመጽሐፍ 1ን የአጀማመር ጠባይ ያክልበታል፣ “ሀሌ ሉያ።”

1. መዝሙር 105 ስለ እስራኤል የዘጸአት ልምምድ ነው የሚገልጸው
2. መዝሙር 106 የሚያመራው ስለ ባቢሎን ስደት መከራ ሁነት ነው
3. መዝሙር 107 የሚናገረው ስለ መመለስ (መታደስ) ነው

ለ. መዝሙራትን መተርጎም ላይ ጠቃሚ የሚሆነው ታሪካዊ መቼቱ ላይ ማስረገጥ ስንሞክር ነው። መዝሙር 107፡1-3 እንድንገነዘብ ይረዳናል፣ ይህ የእግዚአብሔር ማዳን መሆኑን፣ ከባቢሎን ስደት።

ሐ. በዚህ መዝሙር ላይ ተደጋጋሚ ፈርጅ (አገባብ) አለ፣ ከመዝ. 107፡4 ላይ ጀምሮ እስከ ቁጥር 32 የሚቀጥል። በርካታ ተደጋጋሚ ተመሳሳይ አዝማቾች አሉ። ከእነርሱ አንደኛው፣ "በመከራቸው ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ" ነው፣ መዝ. 106:7፣13፣19፣28። ይህ ሐረግ ተመሳሳይነት አለው ከእስራኤል ልምምድ ጋር፣ በዘመነ-መሳፍንት።

መ. ሌላው ተደጋጋሚ አዝማች መዝ. 107:8፣15፣21፣31 ነው። ይህ አዝማች የሚያተኩረው በእስራኤል አምላክ የኪዳን ታማኝነት ላይ ነው። ይኸው ተመሳሳይ ልዩ ቃል፣ *ሄሰድ* (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቸርነት)፣ ይሄንን መዝሙር ይጀምራል ይጨርሳልም። የዚህ አስደናቂ መዝሙር ጭብጥ የያህዌ የጸና የኪዳን ታማኝነት ነው።

ሠ. አራት እጥፍ የማዳን ፈርጅ አለ። አንዳንድ ሊቃውንት የሚያስቡት ይህ የሚዛመደው ወደ ኢየሩሳሌም ጉዞ የሚያደርጉትን መናኞች ነው፣ ነገር ግን ይህ በእጅጉን የማይመስል ነው፣ በተለይም በቁ. 4 ፈርጅ ምክንያት፣ መዝ. 107፡23-31፣ እሱም በባሕር ላይ ንግድን ከማካሄድ ጋር የሚያያዝ። የተሻለ መረዳት የሚሆነው አራቱ ከውድቀት የመታደግ ዘይቤዎች ናቸው።
1. ባለ ቅፍለት ነጋዴዎች፣ በምድረ-በዳ ጠፍተው ሲገኙ፣ መዝ. 107፡4-9
2. በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ የታሰሩ እስረኞች ሲለቀቁ፣ መዝ. 107፡10-16
3. እስከ ሞት ድረስ የሚያደርስ ሕመም፣ ግን ሲፈወስ፣ መዝ. 107፡17-22
4. በባሕር ላይ ብርቱ ማዕበል የሚገጥማቸው፣ ነገር ግን የዳኑ፣ መዝ. 107፡23-31

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 107፡1-3**

**1ቸር ነውና፥ ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
**እግዚአብሔርን አመስግኑ**
**2እግዚአብሔር ያዳናቸው፥**
**ከጠላቶች እጅ ያዳናቸው ይናገሩ።**
**3ከምሥራቅና ከምዕራብ፥**
**ከሰሜንና ከባሕር፥**
**ከየአገሩ ሰበሰባቸው።**

**107፡1 "እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና"** ይህ ተመሳሳይ መጀመሪያ ነው፣ እንደ መዝሙር 106፤ 118፤ እና 136 (ማለትም፣ ቢ.ዲ.ቢ. 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል* ተተኳሪ፤ እሱም ብቸኛው ተተኳሪ ነው፣ በዚህ መዝሙር ላይ)። ይህም በመሠረቱ የታማኝ ተከታይ ርዕዮተ-ዓለም ነው። በምንም ዓይነት ሁኔታ ውስጥ ራሳችንን ብናገኝ፣ እሱ ጥልቅ የሆነ የማይናወጥ እምነት ነው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ለሚያምኑ፣ እግዚአብሔር ከእኛ ጋር፣ እግዚአብሔር ለእኛ ስለ መሆኑ፣ እግዚአብሔር ሊያድነን ይችላል።

▣ **"ምሕረቱ ለዘላለም ነውና"** ይህ የኪዳን ቃል *ሄሰድ* ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት ([ሄሰድ])። እሱም በቀዳሚነት የሚናገረው ስለ እግዚአብሔር ጽኑ፣ ኪዳናዊ ታማኝነት ነው። ይህ መዝሙር የሚጀምረውና የሚጨርሰው (መዝ. 107፡43ለ) በእግዚአብሔር ኪዳናዊ ፍቅር ነው። እግዚአብሔር የኪዳናት አመንጪ ብቻ አይደለም፣ እሱ የኪዳናት ፈጻሚም እንጂ።

ለ"ዘላለም" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (አላም)።

**107፡2 "እግዚአብሔር ያዳናቸው ይናገሩ"** ይህ ቃል የዕብራይስጥ ቃል *ጎል* ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 145፣ ኬቢ 169፣
*ቃል* ተገብሮ አንቀጽ)። እሱም በቀዳሚነት አጽንዖት የሚሰጠው ሀብታም ዘመድ አንዱን ከባርነት መልሶ ሲገዛው ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መዋጀት/መቤዠት)። እነዚህ ግለሰባዊ የቤተሰብ ዘይቤዎች ጥቅም ላይ የዋሉት እግዚአብሔር እጅግ ወዳጃዊና አስፈላጊ መሆኑን ነው፣ ከሰዎች ጋር ባለ ግንኙነት።

የእግዚአብሔር ሰዎች የእግዚአብሔርን ምሕረት እንዲህ እንዲናገሩ ጥሪ ተደርጓል። ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ፣ ይህ ሌላው ሁለንተናዊ ጭብጥ ነው (መዝ. 107:8፣15፣21፣31)።

"ተናገሩ" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 55፣ ኬቢ 65) *ቃል* ያልተጠናቀቀ ነው በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ። ይህ መዝሙር የእነዚህን ሰዋሰዋዊ መልኮች አስራ አንዱን የያዘ ነው (መዝ. 107:2፣ 8፣ 15፣ 21፣ 22 [ሁለቴ]፣ 32 [ሁለቴ፣ 43 [ሁለቴ])።

▣ **"ከጠላቶቻቸው እጅ ያዳናቸው"** በመዝ. 107፡3 ምክንያት ይህ የሚጠቅሰው የሶርያንና የባቢሎንን ስደቶች ነው። የመመለስ ጸሎት እሱም መዝ. 106፡47 እና መዝሙር 107 ላይ የሚገኘው የ'ዛ ጸሎት ፍጻሜ (ምላሽ) ይመስላል።

"እጅ" ለሚለው ዘይቤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ።

**107፡3 “ደቡብ”** ይህ በጥሬው “ባሕር” ለሚለው ቃል ነው (ጄፒኤስኤኤ)። “ባሕር” የሚለው ቃል (ቢዲቢ 410) እና “ደቡብ” የሚለው ቃል (“ቀኝ እጅ፣” ቢዲቢ 411 1) ፊደላቸው በዕብራይስጥ ተመሳሳይ ነው። እነዚህ አራቱ የኮምፓስ ዋነኛ አመልካች ነጥቦች ናቸው፣ ይኸውም ሁለንተናዊ መታደስን የሚገልጹ።

አብዛኞቹ ዘመናዊ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች “ባሕር”ን ወደ “ደቡብ” አሻሽለውታል፣ ምክንያቱም “ምዕራብ” ቀደም ብሎ ስለተጠቀሰ። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 384) ለ “ባሕር” “ሀ” ደረጃ ይሰጠዋል (እጅግ ከፍ ያለ ይሁንታ)። ዋነኛው ጽሑፍ “ባሕር” ከሆነ የሚያመለክተው የታላቁን ባሕር (ሜዲትራኒያን” ደሴቶችን ነው፣ እዚያም የእግዚአብሔር ሕዝብ እንደ እስረኛ/ባሪያ የተወሰደበት።

“መሰብሰብ” የሚለው (ቢዲቢ 867፣ ኬቢ 1062፣ ፒኤል የተጠናቀቀ) የያህዌ መቤዠት መዝሙር 107 ላይ ለመዝ. 106:47 ጸሎት ምላሽ መሆኑን ተገንዘብ (ቢዲቢ 867፣ ኬቢ 1062፣ ፒኤል ተተኳሪ)።

**መዝሙር ፡ 107፡4-9**

**4 ውኃ በሌለበት ምድረ በዳ ተቅበዘበዙ**
**የሚኖሩበትንም ከተማ መንገድ አላገኙም።**
**5 ተራቡ ተጠሙም፥**
**ነፍሳቸውም በውስጣቸው አለቀች።**
**6 በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፥**
**ከመከራቸውም አዳናቸው**
**7 ወደሚኖሩበት ከተማ ይሄዱ ዘንድ**
**የቀና መንገድን መራቸው።**
**8 ለሰው ልጆች ስላደረገው ተኣምራት**
**ስለ ምሕረቱም እግዚአብሔርን ያመስግኑ**
**9 የተራበችን ነፍስ አጥግቦአልና፥**
**የተራቈተችንም ነፍስ በበረከት ሞልቶአልና።**

**107፡4 “ውኃ በሌለበት ምድረ-በዳ ተቅበዘበዙ”** አንዳንዶች ይሄ ግልጽ የሆነው የዘጸአት ጠቃሽ ነው ሊሆ ይችላሉ፣ ሆኖም፣ ቀሪው መዝሙር ከዘጸአት ጊዜ ጋር አይገጥምም። ስለዚህ፣ እኔ የማስበው ይህ ከአራቱ የመጀመሪያው ማስረጃ (ሁኔታ) ነው፣ እሱም እግዚአብሔር ሕዝቡን ከችግር የታደገበት። ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ሠ ተመልከት።

▣ **“የሚኖሩበትንም ከተማ መንገድ አላገኙም።”** “የሚኖሩበት ከተማ” የሚለው የቃላት መለዋወጥ (ጨዋታ) በዚህ መዝሙር በበርካታ ስፍራዎች ላይ ይገኛል (መዝ. 107፡7፣ 36)። እሱም ሊሆን የሚችለው ኢየሩሳሌምን እና የተስፋይቱ ምድርን የሚጠቅስ ነው፣ ግን እሱ በቅድሚያ የሚናገረው የመንገደኞች ማረፊያ፣ መመገቢያ፣ እና ደኅንነት የሚሆን ስፍራ ስለ ማግኘት ነው።

**107፡5** “ነፍስ” (“ኔፊሽ” የሚለው ቃል፣ ቢዲቢ 659፣ ማስታወሻ ተመልከት ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ላይ ዘፍ. 35፡18) የሚገልጸው የሕይወት እስትንፋስ ኃይልን ነው።

1. መዝ. 107፡5 — ነፍሳቸውም በውስጣቸው አለቀች
2. መዝ. 107፡9 — የተጠማች ነፍስ
3. መዝ. 107፡9 — የተራበች ነፍስ
4. መዝ. 107፡18 — ነፍሳቸውም ምግብን ተጸየፈች
5. መዝ. 107፡26 — ነፍሳቸውም ቀለጠች

እነዚህ እያንዳንዳቸው የሚገልጹት በመከራና በጥንቀት ውስጥ ያለን ሰው ነው፣ በሞት አፋፍ ላይ።

**107፡6፤13፤19፤28 “በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፥”** ይህ ፊርጅ የተቀመጠው በእግዚአብሔር ሕዝብ ነው፣ በውድቀት ጊዜ፣ ወደ እርሱ ሲጮኹ እና እግዚአብሔር ሲያድናቸው፣ የሚያሳየው የመሳፍንትን ጊዜ ነው።

**107፡6 “ከመከራቸውም አዳናቸው”** የእግዚአብሔር ማዳን ደግሞ ትይዩ ነው፣ በእነዚህ በአራቱም ሁሉ ዘይቤአዊ ሁኔታዎች (መዝ. 107:6-7፤ 13-14፤ 19-20፤ 28-29)።

**107፡7 “በቀና መንገድ መራቸው”** ይህ የቀና መንገድ ጽንሰ-ሐሳብ የሚያንጸባርቀው የዕብራይስጥን “ሁለቱ መንገዶች” ፈሊጥ ነው (ዘዳ. 30:15-20፤ መዝ. 1:1፤ ማቴ. 7:13-14)። ለያህዌ የእምነትና የታማኝነት ሕይወት ተገልጿል

1. ቀና መንገድ
2. የተስተካከለ መንገድ
3. የለዘበ መንገድ
4. ከማሰናከያ የጸዳ መንገድ

የኃጢአተኛ የሕይወት ስልት የዚህ ተቃራኒ ነው፣ በመከራና በችግር የተሞላ።

ኢሳይያስ አዘውትሮ ይናገራል፣ ያህዌ ለሕዝቡ ስላዘጋጀው ልዩ መንገድ፣ ከስደት ሲመለሱ (ኢሳ. 20:7፤ 35:7-8፤ 40:3-4፤ 42:15-16፤ 43:19-20፤ 49:10-11፤ 57:14፤ 62:10)።

**107:8 "ስለ ምሕረቱም እግዚአብሔርን ያመስግኑ"** *ግሡ* (ቢ.ዲ.ቢ. 392፣ ኬ.ቢ. 389፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕንው መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለው) *መዝ.* 107:8፣15፣21፣31 ላይ ይከሰታል። እዚህም ደግሞ የተደገመው አዝማች አስደናቂው የእግዚአብሔር የኪዳን ፍቅር ነው፣ በልጆቹ ሕይወት ላይ የሚገለጠው። በመከራ ጊዜ እንኳ ቢሆን፣ የእርሱ ታማኝነት ርግጥ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት)።

▣ **"ለሰው ልጆች ስላደረገው ተኣምራት"** ይህ በቅድሚያ የሚያመለክተው ስለ እግዚአብሔር የጸጋ *ሥራዎች* ነው፣ ሕዝቡን ለመታደግ (*መዝ.* 107:24፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተአምራት (አስደናቂ ነገሮች))። ሁለት *መንገዶች* አሉ፣ ይሄንን ሐረግ ለመመልከት። አንደኛው አጽንዖት የሚሰጠው እግዚአብሔርን ነው፣ ለዓለም ሕይወት እንደሚመግብ፣ ለሰው ልጆች ሁሉ ክብካቤ እንደሚያደርግ አምላክ። ነገር ግን፣ እኔ እንደማስበው ይሄንን ለመመልከት የተሻለ *መንገድ* የሚሆነው፣ እስራኤል ለእግዚአብሔር *ሥራ* ምስክር እንዲሆን ነው፣ለዓለም። ይህም ከ*መዝ.* 107:2 ጋር እጅግ በተሻለ ይገጥማል፣ እና ከዩኒቨርሳል አጽንዖት ጋር፣ እናም በዚህ *መዝሙር* ክፍል ካሉት ከአብዛኞቹ *መዝሙራት* ባሕርያት ጋር። እስራኤል እንዲሆን የታሰበው የካህናት *መንግሥት* ነበር፣ ሞላውን ዓለም ወደ እግዚአብሔር የሚመራ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

**107:9 "የተራበችን ነፍስ አጥግቧልና"** ይህ የእግዚአብሔርን አካላዊ *መታደግ* ሊያመለክት ይችላል፣ ለተለየ ሁነት፣ *መዝ.* 107:4-9 ያሉት ላለፉበት፣ ወይም እሱ ሰፋ ላለ መንፈሳዊ መልክ አጠቃላይ ሊሆን ይችላል። ይህ *መዝሙር*፣ በቀላሉ አጠቃላይ ሊሆን ይችላል፣ የሰው ልጆች ሁሉ ለሚገጥማቸው ችግሮች፣ ከዘፍጥረት 3 በኋላ፣ ግን በተለይ የእግዚአብሔር ሕዝብ፣ በጌታ እንደተታመኑ እና እንደዳኑ፣ ለእግዚአብሔር ኃይልና ፍቅር ምስክር እንዲሆኑ፣ ለማያምነው ዓለም።

***መዝሙር* ፡ 107:10-16**

**10በጨለማ በሞትም ጥላ የተቀመጡ፥
በችግር በብረትም የታሰሩ
11የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ዐመፁ፥
የልዑልንም ምክር ስለ ናቁ፥
12ልባቸው በድካም ተዋረደ
ታመሙ የሚረዳቸውም አጡ።
13በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፥
በመከራቸውም አዳናቸው።
14ከጨለማና ከሞት ጥላ አወጣቸው፥
እስራታቸውንም ሰበረ።
15ለሰው ልጆች ስላደረገው ተኣምራት
ስለ ምሕረቱም እግዚአብሔርን ያመስግኑ
16የናሱን ደጆች ሰብሮአልና፥
የብረቱንም መወርወሪያ ቈርጦአልና።**

**107:10 "በጨለማ በሞትም ጥላ የተቀመጡ፥"** "የሞት ጥላ" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 853) *መዝሙር* 23:4 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ፍችውም "ድቅድቅ ጨለማ" (ቢ.ዲ.ቢ. 161 አወቃቀር ቢ.ዲ.ቢ. 853)። እሱም መረዳት ይቸላል፣ በሕይወት ላይ ለሚደርስ ዋነኛ ችግር ወይም አንዱ በሞት አፋፍ ላይ ላለ። በዚህ የተለየ ጉዳይ ግልጽ የሆነው፣ የምንናገረው በጨለማ፣ በጥልቅ ጉድጓድ ውስጥ ስለ ተጣሉ እስረኞች ነው።
ይህ ከአራቱ ታሳቢ የማዳን ትዕይንቶች ሁለተኛው ነው። ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ሠ።

**107:11 "የእግዚአብሔርን ቃል ስለ ዐመፁ፥"** ይህ እጅግ ዓይነተኛ ሐረግ ነው። እነዚህ ውድቀቶች በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የደረሱት እግዚአብሔር ኃይል ስላጣ ወይም ፍቅር ስላጣ አይደለም፣ በሕዝቡ ግልጽ የሆነ ዓመጻ ምክንያት ነው እንጂ በእግዚአብሔር ላይ (*መዝ.* 107:17፣ 34)። ምንም እንኳ ይህ ከአራቱ ታሳቢ ትዕይንቶች ጋር ባይቀመጥም፣ እስራኤል እያዩ ያሉት መከራ የሚያያዘው ከኃጢአታቸው እና ከዓመጻቸው አኳያ መሆኑ ግልጽ ነው፣ በኪዳኑ ላይ (ሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30)።

▣ **"ልዑሉ"** ይህ *መዝሙር* በርካታ ስሞችን ለመለኮት ይጠቀማል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች)።
1. *ያህዌ* – *መዝ.* 107:1፣6፣8፣13፣15፣19፣21፣24፣28፣31፣43
2. *ኤል* – *መዝ.* 107:11
3. ልዑሉ (*ኤሊዮን* ቢ.ዲ.ቢ. 751) – *መዝ.* 107:11

ቁጥር 3 አዘውትሮ እስራኤላውያን ባልሆኑ ጥቅም ላይ ይውላል (ልዑሉ. 14:19፤ ዘኍ. 24:15)። ሙሴ ዘዳ. 32:8 ላይ ተጠቅሞበታል (LXX) ያህዌ ምድርን ለአሕዛብ ስለ ማከፋፈሉ። በዚህ *መዝሙር* ላይ የእርሱ አጠቃቀም የዚህን አጭር ጽሑፍ ዩኒቨርሳላዊ ጠባይ ማስረጃነት ያክላል (ይጨምራል)።

**107:12 "የሚረዳ አጡ"** ይህ አናሳ ሐረግ ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል፣ የሌላ አማልክትን መርዳት አለመቻል ለማሳየት (2 *ነገ.* 14:26፤ *መዝ.* 22:11፤ 72:12፤ ኢሳ. 63:5)። *ያህዌ* ያስረግጣል "ሌላ አምላክ የለም ከእኔ በቀር፣ በእኔ ላይ ካመጻችሁ ምንም ዕርዳታ አታገኙም። ለእኔ ግን ምላሽ ብትሰጡ (ብትታዘዙ)፣ እናንተን ባሪያ የሚያደርግ (የሚጨቁን) በምድር ላይ አይኖርም።" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት።

**107:13 "ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፥"** *መዝ.* 107:6 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"በመከራቸውም አዳናቸው።"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል "*መዳን*" ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 446፣ ኬ.ቢ. 488፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት [የብኪ ቃል])። እሱም በቀዳሚነት የሚያመለክተው *ሥጋዊ* ትድግናን ነው፣ በብኪ። "*መዳን*" የሚለው ቃል *መንፈሳዊ* ገጽታዎችን በአኪ ይወስዳል።

**107፡14** ይህ *ሥጋዊ* ደኅንነትን ይደግማል፣ የእነዚህን እስረኞች፣ መዝ. 107፡10 ላይ የተጠቀሱትን።

**107፡15** ይህ የመዝ. 107፡8ን አጽንዖት ይደግማል። እሱም እንደገና ይደግማል፣ 107፡21 እና 31 ላይ፣ ለአጽንዖት።

"የሰው ልጆች" የሚለው ሐረግ አጠቃቀም ("*ቤን አዳም*")፣ ዩኒቨርሳል ይዘት አለው። ያህዌ፣ የሰዎች ፈጣሪ፣ በአምሳሉ (ዘፍ. 1፡26-27)፣ ደግሞ የሰዎች ሁሉ አዳኝ ነው (ዘፍ. 3፡15፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)። ለእስራኤል ተስፋ አለ፤ ለሁሉም ተስፋ አለ!

**107፡16 "የናሱን ደጆች ሰብሮአልና፥ የብረቱንም መወርወሪያ ቈርጦአልና።"** በጊዜአቸው፣ እነዚህ የብረት ደጆች እጅግ ጠንካሮቹ ታሳቢ የሰው ከለላ ነበሩ። እነዚህ ለእግዚአብሔር ጥንካሬ እና ኃይል ዘይቤዎች ናቸው፣ እሱም ምንም ከለላ የማያግደው፣ ሕዝቡን ለመርዳት (ማለትም፣ ኢሳ. 45፡1-2)።

## መዝሙር ፡ 107፡17-22

17 **ስለ ዓመፃቸው ሰነፉ፥**
**ስለ ኃጢአታቸውም ተቸገሩ።**
18 **ሰውነታቸው መብልን ሁሉ ተጸየፈች፥**
**ወደ ሞትም ደጆች ቀረቡ።**
19 **በተጨነቁ ጊዜም ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፥**
**ከመከራቸውም አዳናቸው።**
20 **ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም፥**
**ከጥፋታቸውም አዳናቸው።**
21 **ለሰው ልጆች ስላደረገው ተኣምራት**
**ስለ ምሕረቱም እግዚአብሔርን ያመሰግኑ**
22 **የምስጋና መሥዋዕትንም ይሠውለት፥**
**በእልልታም ሥራውን ይንገሩ።**

**107፡17 "ተቸገሩ"** ይህ ዘይቤ ነው፣ እስከ ሞት ለሚያደርስ ሕመም። ሆኖም፣ ይህ የግሥ ዓይነት አገናዛቢ ነው እንጂ ተገብሮ አይደለም፣ እናም መተርጎም የሚኖርበት "በራሳቸው ተቸገሩ" በሚል ነው (ቢዲቢ 776፣ ኬቢ 853፣ *ሂዝፓል* ያልተጠናቀቀ)። እንደተባለው፣ የእግዚአብሔርን ሕግ አንሰብርም፣ ነገር ግን ራሳችንን በእግዚአብሔር ሕግ እንሰብራለን እንጂ። በዚህ ጽሑፍ ላይ ብዙ እውነት አለ፣ ስለ እግዚአብሔር ሁለንተናዊ (ዩኒቨርስ) ሞራል።

**107፡18** ይህ የምግብ ፍላጎት ስለማጣት መግለጫ መንገድ ነው፣ ከጽኑ ሕማም የተነሣ። በዚህ ቁጥር ላይ ሲኦል የተገለጸው እንደ ምሽግ ወይም ደጅ እንዳለው ከተማ ነው (ኢዮብ 38፡17)። እጅግ በተደጋጋሚ ሲኦል በሰውኛ ወይም በዘይቤነት በበርካታ መንገዶች ይገለጻል፣ ነገር ግን እየተናገርን ያለነው ስለ ሞት እንደሆነ ግልጽ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው?

**107፡19** ሐረጉ መዝ. 107:6፣13፣19፣ እና 28። እሱም ዘመነ መሳፍንትን የሚያስታውስ ነው።

**107፡20 "ቃሉን ላከ ፈወሳቸውም፥"** እዚህጋ የዕብራይስጡን አጽንዖት ተገንዘቡ፣ በንግግር ቃል ኃይል ላይ። እንደ ዘፍጥረት 1 ባለ መልኩ፣ እግዚአብሔር ይናገራል፣ ያም ይፈጸማል። ተመሳሳይ የሆነ አጽንዖት በእግዚአብሔር ቃል ኃይል ላይ ሊታይ ይችላል፣ ኢሳ. 55፡11 ላይ። ብኪ ላይ እግዚአብሔር ሲናገር፣ ቃሉ ነጻ፣ በራሱ የሚፈጽም ሕላዌ ይሆናል።

"ጥፋቶች" የሚለው ስም ("ጉድጓድ፣" ቢዲቢ 1005) የአልፎ አልፎ ሥር ነው፣ እናም ሦስት ቦታዎች ላይ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ።

1. እዚህ
2. ምሳ. 28፡10
3. ሰቆ. 4፡20

እሱም የሚያመለክተው

1. የጠላቶችን ተንኮልና ዕቅድ (የእንስሳት ወጥመድ)
2. ሞት (ሲኦል እንደ ጉድጓድ)

**107፡21** ይህ ሐረግ መዝ. 107:8፣15፣21፣31። ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 107:8 ላይ።

**107፡22** ይህ ቁጥር አጽንዖት የሚሰጠው ለመቅደስ አምልኮ ነው፣ በኢየሩሳሌም፣ መዝ. 107፡23 ላይ እንዳለው። ደግሞም 107፡2ሀ የሚያንጸባርቀው የመቅደስ ተግባራትን ነው።

## መዝሙር ፡ 107፡23-32

23 **በመርከቦች ወደ ባሕር የሚወርዱ፥**
**በታላቅ ውኃ ሥራቸውን የሚሠሩ፥**
24 **እነርሱ የእግዚአብሔርን ሥራ፥**
**በጥልቅም ያለችውን ድንቁን አዩ።**
25 **ተናገረ፥ ዐውሎ ነፋስም ተነሣ፥**

ሞገድም ከፍ ከፍ አለ።
26ወደ ሰማይ ይወጣሉ ወደ ጥልቅም ይወርዳሉ
ነፍሳቸውም በመከራ ቀለጠች።
27ደነገጡ እንደ ሰካርም ተንገደገዱ፥
ጥበባቸውም ሁሉ ተዋጠች።
28በተጨነቁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኹ፥
ከመከራቸውም አዳናቸው።
29ዐውሎንም ጸጥ አደረገ፥
ሞገዱም ዝም አለ።
30ዝም ብሎአልና ደስ አላቸው
ወደ ፈለጉትም ወደብ መራቸው።
31ለሰው ልጆች ስላደረገው ተአምራት
ስለ ምሕረቱም እግዚአብሔርን ያመስግኑ።
32በሕዝብ ጉባኤ ከፍ ከፍ ያድርጉት፥
በሽማግሌዎችም ሸንጎ ያመስግኑት።

**107፡23 "በመርከቦች ወደ ባሕር የሚወርዱ፥"** አይሁድ አዘውትረው በባሕር *ሥራዎች* ላይ አይጠመዱም። አንድ ምሳሌ ይኖራል፣ 1 ነገ. 9፡27፣28፣ ሰሎሞን ባሕረኞችን ሲያደራጅ በአካባ ባሕረ-ሰላጤ፣ ነገር ግን ይሄንን በማድረጉ ተኮነነ፣ እውነቱም ፍንቄአውያን መርከብ *መሥራታቸውና* መርከበኞችን ማሰማራታቸው ነው። የተሸፈነ ጠቃሽ አለ፣ አንደኛው የአይሁድ ነገድ በባሕር ነክ *ሥራዎች* ውስጥ ስለ መግባቱ፣ መሳ. 5፡17 ላይ፣ ግን በድጋሚ ይህም ምሥጢራዊና ርግጠኛ ያልሆነ ፍች ነው ያለው። አይሁድ እንዲያው በባሕር-ነክ *ሥራዎች* ላይ እጅጉን አይጠመዱም። የመዝ. 107፡23-32 ዘይቤአዊ ዳራ የባሕር ጽኑ ሞገድ ነው፣ እሱም የበረሀ ኗሪዎችን የሚያስፈራ።

ይህ አራተኛው መላ-ምታዊ ሁኔታ ነው፣ የማዳን፤ ዐውድ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ሠ።

**107፡25-27** እነዚህ ስሜት የሚነኩ ዘይቤአዊ ምሳሌዎች ናቸው፣ የባሕር አለመመቸትና ፍራቻ፣ በባሕር ላይ ከሚነሣ ማዕበል ጋር የተያያዙ።

**107፡27** በሁለተኛው ስንኝ ላይ ያለው *ግሥ* በጥሬው "ተዋጡ" የሚል ነው (ቢ.ዲ.ቢ 118፣ *ሂዝፔል* ያልተጠናቀቀ)፣ እሱም የአንድ ነገርን ድንገተኛ ጥፋት የሚገልጽ (ማለትም፣ ባሕር በማዕበል አማካኝነት መርከብን ሲውጥ)።

ኬቢ 135 III *ሥሩን* የሚወስደው "አንዱ እንደተምታታበት ለማሳየት ነው።" ይህ ብቸኛው የዚህ *ሥር* ምሳሌ ነው፣ በ*ሂዝፓል* ላይ፣ ምንም እንኳ ቢሰጥም

1. ኒፋል ኢሳ. 28፡7 ላይ
2. ፔይል ኢሳ. 3፡12፤ 19፡3 ላይ
3. ፑአል ኢሳ. 9፡16 ላይ

በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች ይሄንን *ግሥ* የሚመለከቱት ልምድ ያላቸው ባሕረኞች የባሕር እውቀታቸውን መጠቀም ካለመቻላቸው ጋር በተያያዘ ነው፣ ለማምለጥ ሲፈልጉ።

**107፡30 "*የፈለጉት መጠጊያ*"** ይህ በጥሬው "የፈለጉት ከተማ" ማለት ነው። ይህ "ከተማ" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ 562፣ ኬቢ 568) የሚገኘው እዚህጋ ብቻ ነው። አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች "መጠጊያ" ወይም "ወደብ" የሚል አላቸው። እኔ እንደማስበው "የሚኖሩበት ከተማ" ከሚለው ጋር ትይዩ እንደ ሆነ ነው፣ መዝ. 107፡4 እና 36 ላይ ካለው። እሱም የዕረፍት፣ የመመገቢያ፣ እና የደኅንነት ስፍራ ነው! "የሞት ደጆች" ከሚለው ጋር ይቃረናል (ማለትም፣ *ሲኦል*፣ የሙታን ከተማ)። ባጠቃላይ እግዚአብሔር ብቻ ነው እንዲህ ዓይነት ስፍራ! እሱ ብቻ ነው ዘላለማዊው ከተማ (ዕብ. 11፡10)!

**107፡32 "በሕዝብ ጉባኤ"** ይህ ለእስራኤል የሆነውን ኪዳን ባሕርይ የሚገልጽ ሐረግ ነው።

▣ **"በሽማግሌዎችም ሸንጎ ያመስግኑት።"** አንዳንድ ግምቶች አሉ፣ መዝ. 107፡33-43 የያዘውን በተመለከተ

1. የሕዝብ ቃል ለሽማግሌዎች
2. የሽማግሌዎች ምላሽ ለቃላቸው

የቀጣዮቹ ቁጥሮች ትክክለኛ ጠባይ ምንም ይሁን፣ ከአራትዮሹ ፈርጅ ጋር አይገጥምም፣ መዝ. 107፡4-32 ላይ ካሉት ጋር።

## *መዝሙር* ፡ 107፡33-38

33ወንዞችን ምድረ በዳ፥
የውኃውንም ምንጮች ደረቅ አደረጋቸው
34ከተቀመጡባት ክፋት የተነሣ
ፍሬያማዋን ምድር ጨው አደረጋት።
35ምድረ በዳን ለውኃ መቆሚያ፥
ደረቁንም ምድር የውኃ ምንጮች አደረገ።
36በዚያም ራብተኞችን አስቀመጠ፥
የሚኖርባትንም ከተማ ሠሩ።
37እርሻዎችንም ዘሩ ወይኖችንም ተከሉ፥

**የእህልንም ሰብል አደረጉ።**
**[38]ባረካቸውም እጅግም በዙ**
**እንስሶቻቸውንም አላሳነሰባቸውም።**

**107፡33-43** የእግዚአብሔር ፍርድ የተገለጸ ነው፣ እዚህጋም ዓላማ አለው። ያህ ዓላማ የእግዚአብሔር ሕዝብ መመለስና መባረካቸው ነው። ይህም ከበረከት እና ርግማን ክፍል ጋር እጅግ ይመሳሰላል፣ ሌዋ. 26፡1-13 እና ዘዳግም 27-30 ላይ ካለው።

***መዝሙር* ፡ 107፡39-43**

**[39]እነርሱ በችግር በክፋት በጭንቀት**
***ተዋረዱ እያነሱም ሄዱ***
**[40]በአለቆችም ላይ ኀሣርን፥ አፈሰሰ፥**
***መንገድም በሌለበት በምድረ በዳ አሳታቸው።***
**[41]ችግረኛንም ከችግሩ ረዳው**
**እንደ በጎች መንጋ ወገን አደረገው።**
**[42]ቅኖች ያያሉ፥ ደስም ይላቸዋል**
***ኃጢአትም ሁሉ አፍዋን ትዘጋለች።***
**[43]ጥበበኛ የሆነና ይህን የሚጠብቅ ማን ነው?**
**እርሱ የእግዚአብሔርን ምሕረት ያስተውላል።**

**107፡40፣41 "አለቆች... ችግረኛ"** *የሚናዎች ተገላቢጦሽ አንደኛው የእግዚአብሔር መንገዶች ምልክቶች ባሕርይ ነው፣ ከሰዎች ጋር ባለው። እነዚያ የእስራኤል መሪዎች፣ ሕዝቡን በማሳት የመሩት አሁን ተፈረደባቸው፣ ደሀና ከማኅበረሰቡ መካከል የተገለሉት ደግሞ አሁን ወደ የመቤዣ፣ ጤንነት፣ እና ደኅንነት ስፍራ መጡ።*

*በአንዳንድ ዐውደ-ጽሑፎች "የተቸገሩት" የሚለው የሚያመለክተው የያህዌን ታማኝ ተከታዮች ነው።*

**107፡43ሀ** *ይህ ከአኪ ሐረግ ጋር ተመሳሳይ ነው፣ "ጆሮ ያለው ይስማ" ከሚለው። እግዚአብሔር ዕቅዱን ለሕዝቡ ይገልጣል። እንግዲህ ሕዝቡ በእምነት ምላሽ መስጠት ይኖርበታል። ሆኖም፣ በእነርሱ የእምነት ምላሽ እንኳ ቢሆን፣ ቁልፉ የእነርሱ ታማኝነት አይደለም፣ የእግዚአብሔር ታማኝነት እንጂ (ሕዝ. 36፡27-38)።*

**107፡43ለ** *ይህ የሚያመለክተው ዘዳ. 32፡7ን ነው። የኪዳን ታዛዥነት በረከትን ያመጣል (መዝ. 107፡33-38) ነገር ግን ኪዳንን አለመታዘዝ ርግማንን ያመጣል (መዝ. 107፡39-40)።*

## የውይይት ጥያቄዎች

*ይህ የጥናት* *<u>መመሪያ</u>* *ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡*

*እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።*

1. *አንዳንድ ሊቃውንት ለምን መዝሙር 105፣ 106፣ እና 107 ለምን ተዛማጅ ናቸው ብለው ያምናሉ፣ ምንም እንኳ እነርሱ በተለያዩ ሁለት መጻሕፍት ላይ ቢገኙም (ማለትም፣ ምድቦች) መዝሙር ላይ?*
2. *ሄሰድ የሚለው የዕብራይስጥ ቃል ጠቀሜታው ምንድነው፣ "ቸርነት" በሚል በአዲሱ የአሜሪካን መደበኛ ላይ ፣ "ምሕረት" በሚል ኪንግ ጀምስ ላይ የተተረጎመው፣ በዚህ መዝሙር ላይ አዘውትሮ የሚገኘው?*
3. *የዚህ መዝሙር ታሳቢ ታሪካዊ መቼት ምንድነው፣ መዝ. 107፡2፣3 ላይ በመመሥረት?*
4. *አራትዮሹን የጭንቀት ፈርጅ ግለጽ፣ መዝ. 107፡4-32 ላይ የሚገኘውን። ወደ ኢየሩሳሌም የሚጓዙት መናንያን መንገዳቸው ላይ እነዚህ ችግሮች በቁሙ ይገጥሟቸዋልን፣ ወይስ እነርሱ ዘይቤአዊ ናቸውን፣ ከሕይወት ችግሮች ጋር የሚዛመዱ?*
5. *መዝ. 107፡11፣17 እና 34 እጅግ ዓይነተኛ የሚሆኑት ለምንድነው፣ እስራኤል ከገጠማቸው ችግር ጋር በተያያዘ?*
6. *በአይሁድ አስተሳሰብ ኃጢአትና ሕመም የሚያያዙት እንዴት ነው (መዝ. 107፡17፤ ዮሐንስ 9፡2፤ ያዕቆብ 5፡13)?*

# መዝሙር 108

## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር ድልን እንዲሰጥ ምስጋናና ልመና<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር | የእግዚአብሔር ድል ዋስትና በጠላቶች ላይ | የጸሎት ሥርዓት በብሔራዊ ጠላቶች ላይ ድል ለመንሣት | በጠላቶች ላይ የዕርዳታ ጸሎት | የማለዳ ውዳሴና ብሔራዊ ጸሎት |
| 108:1-6 | 108:1-4 | 108:1-4 | 108:1-4 | 108:1-2 |
| | | | | 108:3-4 |
| | 108:5-6 | 108:5-6 | 108:5-6 | 108:5 |
| | | | | 108:6 |
| 108:7-9 | 108:7-9 | 108:7-9 | 108:7-9 | 108:7 |
| | | | | 108:8 |
| | | | | 108:9 |
| 108:10-13 | 108:10-13 | 108:10-13 | 108:10-13 | 108:10-11 |
| | | | | 108:12-13 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

5. የመጀመሪያው አንቀጽ
6. ሁለተኛው አንቀጽ
7. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙር 108፡1-5 ከመዝሙር 57፡7-11 ላይ የተወሰደ ነው።

ለ. መዝሙር 108፡6-13 ከመዝሙር 60፡5-12 ላይ የተወሰደ ነው።

ሐ. ለሥነ-ትርጓሜያዊ ዝርዝሮች ሙሉውን ማስታወሻ ድረ-ገጽ ላይ የመልከት፣ መዝሙር 57 እና 60 ላይ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡108፡1-6**

**[1]ልቤ ጽኑ ነው፥ አቤቱ፥ ልቤ ጽኑ ነው**
**እቀኛለሁ በክብሬም እዘምራለሁ።**
**[2]በገና ሆይ፥ ተነሥ፥ መሰንቆም**
**እኔም ማልጄ እነሣለሁ።**
**[3]አቤቱ፥ በአሕዛብ መካከል አመሰግንሃለሁ፥**
**በወገኖችም መካከል እዘምርልሃለሁ**

[4]ምሕረትህ በሰማይ ላይ ታላቅ ናትና፥
እውነትህም እስከ ደመናት ድረስ ነውና።
[5]አቤቱ፥ በሰማያት ላይ ከፍ ከፍ በል፥
ክብርህም በምድር ሁሉ ላይ ትሁን።
[6]ወዳጆችህ ይድኑ ዘንድ
በቀኝህ አድን አድምጠኝም።

**108፡1ሀ "ጽኑ"** ይህ *ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 465፣ ኬቢ. 464፣ *ኔፋል አንቀጽ*) የእምነትንና የታማኝነትን ሕይወት ይገልጻል (*መዝ.* 57:8 [*ሁለቴ*]፤112:7) ለእግዚአብሔር ቅን *መንገድ* (*መዝ.* 16:11፤139:24)።
ጽኑ ያልሆነ ምሳሌ *መዝ.* 78፡37 ላይ ተሰጥቷል።

LXX፣ ፔሺታ፣እና ቫልጌት ሐረጉን ይደግሙታል፣ ይኸውም የተወሰነ ተመሳሳይነት በዚህ መዝሙር እና በመዝ. 57:7-11 መካከል መፈጠሩን የሚያሳይ።

ለ "ልብ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ

**108፡1ለ-3** የጽኑ ልብ ባሕርያት የሚሆኑት

1. እዘምራለሁ – ቢ.ዲ.ቢ. 1010፣ ኬቢ. 1479፣ *ቃል ተጓዳኝ*
2. ምስጋና እዘምራለሁ – ቢ.ዲ.ቢ. 274፣ ኬቢ. 273፣ *ፒል ተጓዳኝ*
3. እኔም ማልጄ እነሣለሁ – ቢ.ዲ.ቢ. 734፣ ኬቢ. 802፣ *ሂፊልተጓዳኝ*
4. አመሰግናለሁ – ቢ.ዲ.ቢ. 392፣ ኬቢ. 389፣ *ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
5. ምስጋና እዘምራለሁ — ከቁ. 2 ጋር ተመሳሳይ

**108:1ለ**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በነፍሴም"** |
| **አኪጀቅ** | **"በክብሬም"** |
| **አየተመቅ** | **"ነፍሴ ሆይ ተነሽ"** |
| **አእቅ** | **"ነፍሴ ሆይ ተነሽ"** |
| **አኢመቅ** | **"ክብሬም ይምጣ"** |

አኪጀቅ በጥሬው ነው አየተመቅ፣ አእቅ፣ እና አኢመቅ ግን የመዝ. 57:8ን ትይዩ ይጠቀማሉ ሦስተኛውን የግሡን አጠቃቀም "መነሣት"ን ለማከል (ቢ.ዲ.ቢ. 734፣ ኬቢ. 802)፣ ኤምቲ ላይ ሁለት ጊዜ ተከስቷል።

ልዩ ርዕስ ተመልከት: ክብር። እዚህጋ ቃሉ (ቢ.ዲ.ቢ. 458) ጥቅም ላይ የዋለው ለመዝሙረኛው ሕላዌ ነው (ማለትም፣ ኔፊሽ)። ይህ የ "ክብር" ቃል አጠቃቀም መዝ. 7:5፤16:9፤30:12፤57:8 ላይ ይከሰታል።

NET መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 979) የሚለው ማስተካከያ (ዕርማት) እንደሆነ ነው ከ כבוד (ቢ.ዲ.ቢ. 458) ወደ "ሕይወቴ፣" כבדי (ቢ.ዲ.ቢ. 458)። እሱም ኤቢ. ማጣቀሻ ነው፣ ገጽ 94፣ ነገር ግን ኤቢ. ጥቅሱን በአናዝ የሚጠቀመው "ማክበር" የሚለውን ግሥ ለማብራራት ነው፣ ለያህዌ ጥቅም ላይ የዋለውን፣ እናም ለታሰበው ማስተካከያ ድጋፍ ሳይሆን።

**108፡3** የያህዌ ምስጋና እስከምን እንደሚስፋፋ ተገንዘብ

1. ሕዝቦች
2. አሕዛብ
3. ምድር ሁሉ (መዝ. 108፡5ለ

ዩኒቨርሳላዊው ይዘት በፊተኛው መዝሙር ላይ ያለው በዚህ መሰል ባሕርይ ቀጥሏል! ያህዌ አንዱ እውነተኛ አምላክ ነው፣ ብቸኛው ፈጣሪ፣ ብቸኛው አዳኝ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት (በአንድ አምላክ ማመን)።

**108:4**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ቸርነት"** |
| **አኪጀቅ፣ LXX** | **"ምሕረት"** |
| **አየተመቅ** | **"ጽኑ ፍቅር"** |
| **አእቅ** | **"ኪዳናዊ ፍቅር"** |
| **አኢመቅ** | **"የታመነ ፍቅር"** |
| **ጂፒኤስአኤ** | **"ታማኝነት"** |
| **የተእመቅ** | **"የማይወድቅ ፍቅር"** |

ይህ የተለየ የኪዳን ስም ነው (*ሄሰድ*) የያህዌን *ታማኝነት* የሚገልጽ፣ ለተስፋዎቹ። የሰው ልጅ የመዳረሻው ተስፋ የእግዚአብሔር ምሕረትና ታማኝነት ባሕርይ ነው! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቸርነት (ሄሰድ)።

▣ **"ከሰማያት በላይ"** ትይዩውን ተገንዘብ፣ በቀጣዮቹ ሁለት ስንኞች። የያህዌ ቸርነትና እውነት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ *ማመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ*) ከሰማያት በላይ ይደርሳል። አዎን፣ ያህዌ ራሱ ከሥጋዊ ፍጥረት በላይ ነው (*መዝ.* 108፡5)። "ሰማያት" ከምድር በላይ ያለ ከባቢ አየር ነው፣ የያህዌ ማደሪያ ስፍራ ሳይሆን። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማይ እና ልዩ ርዕስ፡ ሦስተኛው ሰማይ።

**108፡5 "ክብር"** *መዝ.* 108፡1 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።

**108፡6 “ወዳጆችህ”** እዚህጋ፣ ይህ የሚያመለክተው የኪዳኑን ሕዝብ ነው (መዝ. 60:5፤127:2፤ ኤር. 11፡15)። እሱም ለመሲሑ መጠሪያ ሆኗል (በተለይም ከኢሳይያስ የአገልጋይ መዝሙር ላይ፣ ማለትም፣ ኢሳ. 42፡1)። ያህዌ ወደ ኢየሱስ ያመለክታል፣ በዚህ ስም

1. በጥምቀቱ — ማቴ. 3፡17
2. ከኢሳይያስ በተጠቀሰው — ማቴ. 12፡18
3. በመቀየሩ ጊዜ — ማቴ. 17፡5

እሱም ኋላ ላይ የቤተሰብ ደግነት መጠሪያ ሆነ፣ ኢየሱስን ለሚከተሉት (ማለትም፣ ሮሜ. 1:7፤ቆላ. 3:12፤1 ተሰ. 1:4፤2 ተሰ. 2:13)።

▣ የመጀመሪያው አንጓ በርካታ ተተኳሪዎች አሉት።

1. ተነሥ፣ በገና እና መሰንቆ፣ መዝ. 108:2 – ቢዲቢ 734፣ ኬቢ 802፣ ቃል
2. አቤቱ አምላክ ከፍ ከፍ በል፣ መዝ. 108:5 – ቢዲቢ 926፣ ኬቢ 1202፣ ቃል
3. አድን፣ መዝ. 108:6 – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ ሂፊል
4. አድምጥ፣ መዝ. 108:6 – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ ቃል

ቁጥር 3 እና 4 የጸሎት ጥያቄዎች ናቸው። ቁጥር 1 እና 2 ከምስጋና ጋር ዝምድና አላቸው።

**መዝሙር ፡108፡7-9**

**7እግዚአብሔር በቅድስናው ተናገረ።**
**ደስ ይለኛል፥ ሴኬምንም እካፈላለሁ፥**
**የሱኮትንም ሸለቆ እሰፍራለሁ።**
**8ገለዓድ የእኔ ነው ምናሴም የእኔ ነው**
**ኤፍሬም የራሴ መጠጊያ ነው።**
**ይሁዳ ንጉሤ ነው።**
**9ሞዓብ መታጠቢያዬ ነው፥**
**በኤዶምያስ ላይም ጫማዬን እዘረጋለሁ**
**ፍልስጥኤም ይገዙልኛል።**

**108፡7-9** ያህዌ ይናገራል (በርካታ ተጓዳኞች) ከመቅደሱ (“ከማደሪያው ድንኳን”) እሱ የከነአን ባለቤት ስለመሆኑ። ይህ አንጓ ከመዝ. 60፡6-8 ነው። አንዳንዶቹ አንጓዎች መፈክር፣ አባባል፣ ወይም የአምልኮ ደንብ ሆነዋል።

**108፡8 “ይሁዳ ንጉሤ ነው”** ይህ ጠቃሽ ነው ያዕቆብ ልጆቹን የባረከበት፣ ዘፍጥረት 49 ላይ፣ በተለይም ዘፍ. 49፡10። ይህም ደግሞ ዘኍ. 24:17 (መዝ. 60:7) ላይ ተጠቅሷል።

**መዝሙር ፡108፡10-13**

**10ወደ ጽኑ ከተማ ማን ይወስደኛል?**
**ማንስ እስከ ኤዶምያስ ይመራኛል?**
**11አቤቱ፥ የጣልኸኝ አንተ አይደለህምን?**
**አምላክ ሆይ፥ ከሠራዊታችን ጋር አትወጣም።**
**12በመከራችን ረድኤትን ስጠን**
**የሰውም ማዳን ከንቱ ነው።**
**13በእግዚአብሔር ኃይልን እናደርጋለን**
**እርሱም የሚያስጨንቁንን ያዋርዳቸዋል።**

**108፡10-13** ያህዌ የተስፋይቱ ምድር ባለቤትና ተቆጣጣሪ ከመሆኑ የተነሣ (ማለትም፣ ከነአን)፣ እሱ በርግጥ ሕዝቡ እንዲሸነፉና እንዲፈናቀሉ አይፈቅድም!

**108፡10 “ጽኑ ከተማ”** ኤምቲ “የተመሸገ ከተማ” የሚል አለው (ቢዲቢ 747 አወቃቀር ቢዲቢ 131)። ይህ የሚጠቅሰው ቦዝራ ከተማን ሊሆን ይችላል፣ ምክንያቱም ኤዶም በቀጣዩ የቅኔ ስንኝ በመጠቀሱ። ቦዝራ (ቢዲቢ 131 II) ከተመሳሳይ የዕብራይስጥ ሥር ነው፣ እንደ “ከተማ” ወይም “ምሽግ” (ቢዲቢ 131፣ አይቪፒ *መጽሐፍ ቅዱስ ዳራ ሐተታ* ተመልከት ገጽ 551)።

**108፡11** የኪዳኑ ሕዝብ በጦርነት ተሸንፈዋል (መዝ. 44፡9) ያህዌ ከእነርሱ ጋር ስላልወጣ (ስላልተጎዳኘ)። ታቦቱ ወደ ጦርነት ይወሰዳል፣ ለያህዌ አካላዊ መገኘት ተምሳሊት እንዲሆን፣ ከወታደሮች ጋር። ነገር ግን ሕዝቡ ለኪዳኑ ታማኝ አለመሆናቸው ከተረጋገጠ፣ ድሉን አይሰጣቸውም።

**108፡12** ይህ እውቅና መስጫ ነው፣ የእስራኤል ብቸኛው ተስፋ ያህዌ ለመሆኑ። የእነርሱ ወታደራዊ ብርታትና ስትራቴጂ ድልን አያመጣም፣ ያህዌ ብቻ ነው የሚችለው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ሁለቱ ተናጋሪዎች እነማናቸው፣ እዚህ መዝሙር ላይ?
2. ከየትኞቹ ሌሎች መዝሙራት ነው ይህ መዝሙር የመጣው?
3. መዝ. 108፡7-9 ለመግለጽ የሚሞክረው ምንድነው?
4. መዝ. 108፡11-12 ላይ የተጠቀሱት ዋነኛ እውነቶች ምንድናቸው?

# መዝሙር 109
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| በጠላቶች ላይ የሚሆን በቀል<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ የዳዊት መዝሙር | በሐሰተኛ ከሳሾች ላይ ፍርድን መለመን | ከግል ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት (ሰቆቃ) | በችግር ላይ ያለ ሰው ልመና | ክፉ የሚያደርገውን ማውገዝ |
| 109:1-5 | 109:1-5 | 109:1-5 | 109:1-5 | 109:1-3 |
| | | | | 109:4-5 |
| 109:6-13 | 109:6-13 | 109:6-19 | 109:6-15 | 109:6-7 |
| | | | | 109:8-9 |
| | | | | 109:10-11 |
| | | | | 109:12-13 |
| 109:14-20 | 109:14-20 | | | 109:14-15 |
| | | | 109:16-19 | 109:16-17 |
| | | | | 109:18-19 |
| | | 109:20-25 | 109:20-25 | 109:20-21 |
| 109:21-25 | 109:21-25 | | | |
| | | | | 109:22-23 |
| | | | | 109:24-25 |
| 109:26-29 | 109:26-29 | 109:26-31 | 109:26-29 | 109:26-27 |
| | | | | 109:28-29 |
| 109:30-31 | 109:30-31 | | 109:30-31 | 109:30-31 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙረኛው አላግባብ የተያዘ ይመስለዋል፣ በሚወዳቸው ሰዎች (የመጀመሪያው አንጓ፣ መዝ. 109፡1-5)።

1. ቃላቸው
   ሀ. ኃጢአተኛ፣ መዝ. 109፡1
   ለ. ተሳዳቢዎች፣ መዝ. 109፡1
   ሐ. ውሸታሞች፣ መዝ. 109፡2
   መ. የጥላቻ ቃላት፣ መዝ. 109፡3
   ሠ. ከሳሽ፣ መዝ. 109፡4
2. ድርጊታቸው
   ሀ. ያለ ምክንያት የሚዋጉኝ፣ መዝ. 109፡3
   ለ. በመልካም ፈንታ ክፉ የሚመልሱ፣ መዝ. 109፡5
   ሐ. በፍቅር ፈንታ ጥላቻ የሚመልሱ፣ መዝ. 109፡5

3. ይህ የፍርድ ቤት ትዕይንትን የሚያንጸባርቅ ይሆናል፣ መዝሙረኛው በሐሰት የተከሰሰበትን (መዝ. 109፡6-7

ለ. እሱም ተከታታይ የሆኑ ፍርዶችን ይለምናል (ተጽዕኖዎች) በጠላቶቹ ላይ (ሁለተኛውና ሦስተኛው አንጓ፣ መዝ. 109፡6-13፣ 14-20)።

1. ከሳሽ በቀኙ ይቁም፣ መዝ. 109፡6-ቢዲቢ 763፣ ኬቢ 840፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. በደለኛ ሆኖ ይገኝ፣ መዝ. 109:7 – ቢዲቢ 422፣ ኬቢ 425፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. ጸሎቱ ኃጢአት ትሁንበት መዝ. 109:7 – ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
4. ዘመኖቹ ጥቂት ይሁኑ፣ መዝ. 109:8 – ከቁ. 3 ጋር ተመሳሳይ
5. ሹመቱን ሌላ ይውሰደው፣ መዝ. 109:8 – ቢዲቢ 542፣ ኬቢ 534፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
6. ልጆቹ ደሀ-አደግ ይሁኑ፣ መዝ. 109:9 – ከቁ. 3 ጋር ተመሳሳይ
7. ሚስቱ መበለት ትሁን፣ መዝ. 109:9 – ከቁ. 3 ጋር ተመሳሳይ
8. ልጆቹም ይንከራተቱ፣መዝ. 109:10 – ይህ ያልተወሰነ ፍጹም ነው እና ያልተጠናቀቀ ግሥ ከተመሳሳይ ሥር (ቢዲቢ 631፣ ኬቢ 681)፣ ይኸውም በሰዋሰዋዊ መንገድ ጽኑዕነትን ማሳያ
   ሀ. መለመን – ቢዲቢ 981፣ ኬቢ 1371፣ ፒል የተጠናቀቀ
   ለ. የሚመገቡትን ይፈልጉ – ቢዲቢ 205፣ ኬቢ 233፣ ቃል የተጠናቀቀ
   አአመመቅ የመዝ. 109:10 የተጠናቀቁዎች የሚተረጉማቸው እንደ ተጽዕኗዊ ነው (ማለትም፣ "ይሁን…")።
9. ባለ ዕዳም ያለሁን ሁሉ ይበርብረው፣ መዝ. 109:11 – ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 723፣ ፒል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
10. እንግዶችም ድካሙን ሁሉ ይበዝብዙት፣ መዝ. 109:11 – ቢዲቢ 102፣ ኬቢ 117፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
11. የሚያግዘውም አያግኝ፣ መዝ. 109:12 – ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ ቃል ተጽዕኗዊ
12. ለደሀ-አደግ ልጆቹ የሚራራ አይገኝ፣ መዝ. 109:12 – ከቁ. 11 ጋር ተመሳሳይ
13. ልጆቹ ይጥፉ፣ መዝ. 109:13 – ከቁ. 11 ጋር ተመሳሳይ
14. ስማቸውም ይደምሰስ፣ መዝ. 109:13 – ቢዲቢ 562፣ ኬቢ 567፣ ኒፋል ተጽዕኗዊ
15. የአባቱ ኃጢአት ትታሰብ፣ መዝ. 109:14 – ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269፣ ኒፋል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
16. የእናቱም ኃጢአት አትደምሰስ፣ መዝ. 109:14 – ቢዲቢ 562፣ ኬቢ 567፣ ኒፋል ተጽዕኗዊ
17. በእግዚአብሔር ፊት ሁልጊዜ ይኑሩ፣ መዝ. 109:15 – ከቁ. 3 ጋር ተመሳሳይ
18. መታሰቢያቸው ከምድር ይጥፋ፣ መዝ. 109:15 – ቢዲቢ 503፣ ኬቢ 500፣ ሂፊል ተጽዕኗዊ
19. እንደሚለብሰው ልብስ ይሁነው (ማለትም፣ ርግማን)፣ መዝ. 109:19 – ከቁ. 11 ጋር ተመሳሳይ
20. አአመመቅ፣ አኪጆቅ፣ አኢመቅ መዝ. 109:20ሀ ን የሚተረጉሙት እንደ ሌላ ተጽዕኗዊ ነው፣ ነገር ግን እሱ ቃል አንቀጽ ነው

ሐ. መዝሙር 109:16-18 ያህዌ ለምን እንደሚፈርድለት ምክንያቱን ይዘረዝራል።

1. ምሕረትን ያደርግ ዘንድ አላሰበምና፣ መዝ. 109:16
2. ችግረኛና ምስኪኑን አሳደደ፣ መዝ. 109:16
3. መርገምን ወደደ፣ መዝ. 109:17
4. መርገምን እንደ ልብስ ለበሳት፣ መዝ. 109:18

መ. መዝሙር 109፡21-25 ላይ መዝሙረኛው ፍላጎቱን ይገልጻል፣ ዕርዳታንም ይጠይቃል (ተቃራኒውን መስተዋድድ ተገንዘብ፣ "ግን ላንተ ብቻ ነው፣ አምላክ ሆይ")።

1. ምሕረትህን በእኔ ላይ አድርግ – ቢዲቢ 793፣ ኬቢ 889፣ ቃል ተተኳሪ
2. አድነኝ – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ ሂፊል ተተኳሪ

እሱ ጸሎቱን የመሠረተው

1. በያህዌ ስም ሲል፣ መዝ. 109:21
2. በያህዌ ቸርነት ላይ፣ መዝ. 6:4፤44:26፤109:21፣26፤119:149
3. በሚያስፈልገው ነገር
   ሀ. እኔ ችግረኛና ምስኪን ነኝና
   ለ. ልቤ ቆስሏል
   ሐ. እንደ ጥላ አልፌአለሁ
   መ. እንደ አንበጣም እረገፍኩ
   ሠ. ጉልበቶቼ በጾም ደከሙ
   ረ. ሥጋዬም ከሳ
   ሰ. ለነውር ሆንኩ

ሠ. መዝ. 109፡26-29 መዝሙረኛው ጸሎቱን ቀጥሏል፣ ፍላጎቱንም ለያህዌ ይገልጻል፣ በጠላቶቹ ላይ እንዲፈርድለት።

1. ዕርዳኝ – ቢዲቢ 740፣ ኬቢ 810፣ ቃል ተተኳሪ
2. እንደቸርነትህ ብዛት አድነኝ – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ መዝ. 109:21
3. ለያህዌ ይጸልያል
   ሀ. ፍርዳቸው ከእርሱ ዘንድ እንደሆነ ይወቁ – ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
   ለ. ይራገማሉ በመባረክ ፈንታ – ቢዲቢ 886፣ ኬቢ 1103፣ ፒል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ እሱም ከያህዌ ተቃውሞ የሚያስነሣ (ማለትም፣ ለበረከት አይሆኑም)
   ሐ. ይፈሩ – ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ (አኪጆቅ፣ አየተመቅ)፣ ተቃርኗዊ ዓረፍተ-ነገር መዝ. 109:28ሀ ላይ እንዳለ፣ እንዲሁ ደግሞ 109:28ሐ ላይ

መ. ከሳሾቹ እፍረትን ይልበሱ – ቢ.ዲ.ቢ. 527፣ ኬቢ. 519፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ* (አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣ አየተመቅ)
ሠ. እፍረታቸውን እንደ መጎናጸፊያ ይልበሱ – ቢ.ዲ.ቢ. 741፣ ኬቢ. 813፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ* (አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣ አየተመቅ)

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፥109፥1-5**

**[1]አምላክ ሆይ፥ ምሥጋናዬን**
**ዝም አትበል፥**
**[2]የኃጢአተኛ አፍና የተንኰለኛ አፍ በላዬ ተላቅቀውብኛልና**
**በሽንገላ አንደበትም በላዬ ተናገሩ**
**[3]በጥል ቃል ከበቡኝ፥**
**በከንቱም ተሰለፉብኝ።**
**[4]በወደድኋቸው ፋንታ አጣሉኝ፥**
**እኔ ግን እጸልያለሁ።**
**[5]በመልካም ፋንታ ክፉን**
**በወደድኋቸውም ፋንታ ጠላትነትን መለሱልኝ።**

**109፥1 "የምስጋናዬ አምላክ ሆይ"** ይህ ሐረግ እዚህጋ እና ዘዳ. 10፥21 ላይ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ነገር ግን ጽንሰ-ሐሳቡ ተደጋጋሚ ነው (ማለትም፣ መዝሙር 146-148)። LXX ይሄንን ሐረግ የሚተረጉመው "ምስጋናዬህ ዝም ብለህ አትለፍ" በሚል ነው።

▣ **"ዝም አትበል"** ይህ የዕብራይስጥ ልመና ነው፣ ያህዌ ጸሎቱን እንዲሰማና ምላሽ እንዲሰጠው (መዝ. 28፡1፤35፡22፤38፡12፤83፡1)።

**109፥2-3** በቃላት ላይ ኃይል አለ፣ በሁለቱም በመባረክም ሆነ በመጉዳት። ቃላታችን ልባችንን ይገልጻሉ! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የሰው ንግግር።
ኤቢ (ገጽ 100) እነዚህን ቁጥሮች የሚመለከተው እንደ እንስሳት ጥቃት ጠቃሽ ነው።
1. የአጥቂ እንስሳት አፍ (መዝ. 22፡14፤ ሰቆ. 3፡46-47)
2. "የሚነጋገሩ" (ቢ.ዲ.ቢ. 180) "የሚነጥቁ" በሚል መልኩ
3. "የሚከብቡ" እንደ እንስሳት መንጋ

**109፥4-5** መጠቃት በጣም የሚጎዳ ነው ነገር ግን በተማመኗቸውና በወዳጆች መጠቃት ደግሞ ድርብ ጉዳት ያለው ነው (መዝ. 35፡12፤38፡20)።

**መዝሙር ፥109፥6-13**

**[6]በላዩ ኃጢአተኛን ሹም**
**ሰይጣንም በቀኙ ይቁም።**
**[7]በተምዋገተም ጊዜ ተረትቶ ይውጣ**
**ጸሎቱም ኃጢአት ትሁንበት።**
**[8]ዘመኖቹም ጥቂት ይሁኑ**
**ሹመቱንም ሌላ ይውሰድ።**
**[9]ልጆቹም ድሀ አደግ ይሁኑ፥**
**ሚስቱም መበለት ትሁን።**
**[10]ልጆቹም ተናውጠው ይቅበዝበዙ ይለምኑም፥**
**ከስፍራቸውም ይባረሩ።**
**[11]ባለዕዳም ያለውን ሁሉ ይበርብረው፥**
**እንግዶችም ድካሙን ሁሉ ይበዝብዙት።**
**[12]የሚያግዘውንም አያግኝ።**
**ለድሀ አደግ ልጆቹም የሚራራ አይኑር።**
**[13]ልጆቹ ይጥፉ**
**በአንድ ትውልድ ስሙ ይደምሰስ።**

**109፥6-20** እነዚህ ሁለት አንጓዎች ለዘመናዊዎቹ ሰዎች እጅግ ከባድ ድምጸት አላቸው። መዝሙረኛው የኪዳን ርግማኖችን እየጠየቀ ነው ያለው (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30) በእምነተ-ቢስ እስራኤላውያን ላይ፣ በጠላቶቹ ላይ እውን እንዲሆን። እሱ ከያህዌ በኩል እንደሆነ ይሰማዋል፤ እሱን ማጥቃት ማለት ያህዌን ማጥቃት ነው።
የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 1407) የሚለው ይህ ረጅሙ የርግማን ክፍል ነው፣ መዝሙር ላይ። እሱም እጅግ ምስል ከሳችና ዘይቤአዊ ነው፣ አንዳንድ አታቾች እንደሚያስቡት የሚያንጸባርቀው ጠላቶች በመዝሙረኛው ላይ የሚሉትን ነው (ማለትም፣ ጀሮም መጽሐፍ

ቅዱስ ሐተታ፣ አኪ.መቅ፣ እና አኪ.ቅ ግርጌ ማስታወሻ)። ሆኖም፣ ይህ ኤምቲ ላይ ሊረጋገጥ አልቻለም። ብቸኛው ማስረጃ የሚሆነው የነጠላ ቁጥር መልኩ ነው፣ በመዝ. 109፡6-19 ጥቅም ላይ የዋለው፣ እሱም የወል ነጠላ ቁጥር ሊሆን የሚችል።

**109፡6 "ከሳሽ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 966፤ መዝ. 109:20፤29) እሱም ለአካላዊው ክፉ፣ ሰይጣን መጠሪያ የሆነ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰይጣን።

**109፡8 "ሹመት"** ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ ይህ ቃል ምን ማለት እንደሆነ (ቢ.ዲ.ቢ. 824) ርግጠኝነት የለም። እሱም "የተከማቸ ፍጆታ"ን ሊጠቅስ ይችላል፣ ኢ.ሳ. 15፡7። አጥቂው ሁነኛ ስፍራ እና ሥልጣን አለው። ይህ ሐረግ (ከመዝ. 69፡25 ለLXX አኳያ) ሐዋ. 1፡20 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ የአስቆሮቱ ይሁዳን ለመጥቀስ። ሐዋርያት ሥራ "ሹመት" የሚለውን ቃል የተጠቀመበት፣ በይሁዳ ምትክ ለሐዋርያነት ከመምረጥ ጋር በተያያዘ ነው።

## መዝሙር ፡109፡14-20

**14 የአባቶቹ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት ትታሰብ**
**የእናቱም ኃጢአት አትደምሰስ።**
**15 በእግዚአብሔር ፊት ሁልጊዜ ይኑሩ**
**መታሰቢያቸው ከምድር ይጥፋ።**
**16 ምሕረትን ያደርግ ዘንድ አላሰበምና**
**ችግረኛንና ምስኪንን ልቡ የተሰበረውንም ሰው**
**ይገድል ዘንድ አሳደደ።**
**17 መርገምን ወደደ ወደ እርሱም መጣች**
**በረከትንም አልመረጠም ከእርሱም ራቀች።**
**18 መርገምን እንደ ልብስ ለበሳት፥**
**እንደ ውኃም ወደ አንጀቱ፥**
**እንደ ቅባትም ወደ አጥንቱ ገባች።**
**19 እንደሚለብሰው ልብስ።**
**ሁልጊዜም እንደሚታጠቀው ትጥቅ ይሁነው።**
**20 ይህ ሥራ ከእግዚአብሔር ዘንድ በሚያጣሉኝ**
**በነፍሴም ላይ ክፉን በሚናገሩ ነው።**

**109፡14-15** ይህ የሁለቱ መጻሕፍት ጠቃሽ ሊሆን ይችላል (ማለትም፣ የድርጊቶች መጽሐፍ እና የሕይወት መጽሐፍ) ይኸውም የእግዚአብሔርን ማስታወስ ተምሳሊት የሚሆኑ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሁለቱ መጻሕፍት።

**109፡17-19** እርግማኖቹ የሚያመለክቱት ለቅጣት ወደ እግዚአብሔር የሚደረገውን ጸሎት ነው። መዝሙረኛው ይጠይቃል፣ የአሳዳጆቹ የበቀል ጸሎት በራሳቸው ላይ እንዲመለስ። ብኪ ላይ አንዱ ፍርድ ቤት ሐሰተኛ ምስክር ሆኖ ቢገኝ፣ በሐሰት የተከሰሰውን ሰው ቅጣት ይቀበላል።

**109፡20** ይህ የመዝ. 109፡6-19 ማጠቃለያ መደምደሚያ ነው። እሱም ከ109፡6-19 ጋር አብሮ ሊሄድ ይችላል (ማለትም፣ አአመመቅ፣ አኪ.ጀቅ) ወይም ከቀጣዩ አንጓ ጋር (አየተመቅ፣ አእቅ፣ አኪ.መቅ)።

## መዝሙር ፡109፡21-25

**21 አንተ ግን አቤቱ ጌታዬ፥ ስለ ስምህ ምሕረትህን በእኔ ላይ አድርግ**
**ምሕረትህ መልካም ናትና አድነኝ።**
**22 እኔ ችግረኛ ምስኪንም ነኝና፥**
**ልቤም በውስጤ ደነገጠብኝ።**
**23 እንዳለፈ ጥላ አለቅሁ፥**
**እንደ አንበጣም እረገፍሁ።**
**24 ጕልበቶቼ በጾም ደከሙ**
**ሥጋዬም ቅቤ በማጣት ከሳ።**
**25 እኔም በእነርሱ ዘንድ ለነውር ሆንሁ**
**ባዩኝ ጊዜ ራሳቸውን ነቀነቁ።**

**109፡21 "ስለ ስምህ"** ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (መዝ. 23:3፤25:11፤31:3፤79:9፤106:8)። ስም ማንነትን ይወክላል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ "ስም"።

**109፡24** ይህ ቁጥር በሁለት መንገዶች ሊተረጎም ይችላል (ዩቢኤስ ማስታወሻ ተመልከት፣ ገጽ 944)።

1. መዝሙረኛው በፍቃዱ እየጾመ ነው
2. መዝሙረኛው ምንም የለውም
   ሀ. ማለፊያ ምግብ
   ለ. የወይራ ዘይት፣ ለመቀባት

**109፡25 *"ራሳቸውን ይነቀንቃሉ"*** ይህ የመናቅ የአካል ንቅናቄ ነው (2 ነገ. 19:21፤ ኢዮብ 16:4፤ መዝ. 22:7፤ኢሳ. 37:22፤ኤር. 18:16፤48:27፤ሰቆ. 2:15፤ማቴ. 27:39፤ማርቆስ 15:29)።

***መዝሙር* ፡109፡26-29**

**[26]አቤቱ አምላኬ፥ እርዳኝ፥**
**እንደ ምሕረትህም አድነኝ።**
**[27]አቤቱ፥ እጅህ ይህች እንደ ሆነች፥**
**አንተም ይህችን እንዳደረግህ ይወቁ።**
**[28]እነርሱ ይራገማሉ አንተ ግን ባርክ**
**በእኔ ላይ የሚነሡ ይፈሩ፥**
**ባሪያህ ግን ደስ ይበለው።**
**[29]የሚያጣሉኝ እፍረትን ይልበሱ**
**እፍረታቸውን እንደ መጐናጸፊያ ይልበሱአት።**

**109፡27** ይህ የሚታወቅ የብኪ ማሳያ ነው፣ ለተገላቢጦሽ ሐሳብ። መዝሙረኛው ንጹሕነቱ በያህዌ እንዲረጋገጥ ይሻል፣ በጠላቶቹ ፊት (መዝ. 23፡ 5)።

**109፡28 *"ባሪያህ"*** "ባሪያ" የሚለው ስም (ቢዲቢ 713) ጥቅም ላይ ሊሆን የሚችለው

1. አገልጋይ
2. የንጉሥ አጃቢ
3. ምዕመናን (ዘዳ. 32:36፣43)
4. ሌዋውያን ዘማሪዎች (መዝ. 113:1፤134:1፤135:1)
5. እስራኤል (ኢሳ. 41:8-9)
6. ቢዲቢ 714፣ ቁ. 6፣ የሚለው እዚህጋ አጠቃቀሙ እግዚአብሔርን በትሕትና መቅረብ ነው (መዝ. 19:11፣13፤27:9፤31:16፤35:27፤ 69:17፤143:2)
7. አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 856) እሱን የሚመለከተው እንደ ዳዊታዊው መሲሕ ማጣቀሻ ነው (መዝ. 78:20፤ኢሳ. 42:1)
8. ለመሪዎች የተለየ መጠሪያ
   ሀ. አብርሃም – ዘፍ. 26:24
   ለ. ይስሐቅ – 24:14
   ሐ. ያዕቆብ – ሕዝ. 28:25፤37:25
   መ. ሙሴ– ዘኊ. 12:7፤ዘዳ. 34:5
   ሠ. ኢያሱ – ኢያ. 24:29 (ከሞቱ በኋላ)
   ረ. ዳዊት – 2 ሳሙ. 3:18፤7:5፣8፣26

***መዝሙር* ፡109፡30-31**

**[30]እግዚአብሔርን በአፌ እጅግ አመሰግነዋለሁ።**
**በብዙዎችም መካከል አከብረዋለሁ**
**[31]ነፍሱን ከሚያሳድዱአት ያድን ዘንድ**
**በድሀ ቀኝ ቆሞአልና።**

**109፡30-31** መዝሙረኛው ያህዌን ያመሰግናል፣ ስለ ታማኝነቱና ስለ ፍርዱ።

1. እግዚአብሔርን በአፌ እጅግ አመሰግነዋለሁ – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ሂፊልያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. አመሰግነዋለሁ – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ፒል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

**109:31 *"በደሀ ቀኝ ቆሟልና"*** ይህ ቀጥተኛ ተቃርኖ ነው፣ ለኃጢአተኛ ከሳሹ፣ መዝ. 109:6 ላይ ላለው። ይኸው ተመሳሳይ ሐረግ ለሰይጣን ዘካ. 3:1 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የእግዚአብሔር ዝምታ አንድምታው ምንድነው?
2. የኃጢአተኛን ድርጊቶች ዘርዝር።
3. በርካታ ተንታኞች ለምን ጠላቶቹ የቅርብ ወዳጆች እንደሆኑ ያስባሉ?
4. አንዱ እንዴት ማስረዳት ይችላል፣ በሌላ ሰው ላይ ዓመጽ መፈለጉን?
5. መዝ. 109፡14 ከሕይወት መጽሐፍ ጽንሰ-ሐሳብ ጋር እንዴት ይዛመዳል?

# መዝሙር 110
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ ለንጉሥ አዛዝን ይሰጠዋል<br><br><u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>የዳዊት መዝሙር | የመሲሑ ግዛት አዋጅ | ጌታ ለንጉሥ ድልን ተስፋ ሰጥቶታል<br>(ንጉሣዊ መዝሙር) | ጌታ እና እሱ የመረጠው ንጉሥ | ካህኑ መሲሕ |
| 110:1-3 | 110:1-2 | 110:1 | 110:1-3 | 110:1 |
| | | 110:2-4 | | 110:2 |
| | 110:3-4 | | | 110:3 |
| 110:4-7 | | | 110:4 | 110:4 |
| | 110:5-7 | 110:5-7 | 110:5-7 | 110:5-7 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይሄንን መዝሙር መተርጎም አስቸጋሪ ነው፣ ምክንያቱም ትክክለኛውን ታሪካዊ መቼት ስለማናውቀው። መጠነኛ ማስረጃ ይኖራል፣ ዋነኛ ካልሆነው፣ ተመስጧዊ ካልሆነው ከዚህ መዝሙር ርዕስ፣ "የዳዊት መዝሙር።" የኢየሱስ ማረጋገጫ ለዚህ፣ ማቴ. 22፡41-46፤ ማርቆስ 12:35-37፤ሉቃስ 20:41-44 ላይ፤ እና ሌሎች ብዙ ስፍራዎች፣ አኪ ላይ የሚያመለክቱት የዚህን መዝሙር ጠቀሜታ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ደግሞ ታሪካዊ መቼቱ በዳዊት ሕይወት ላይ ሊሆን ይችላል። ይህ መዝሙር አኪ ላይ ከሌላው መዝሙር ይልቅ ተጠቅሷል (ማለትም፣ እሱም እንደ መሲሐዊ የሚታይ ሲሆን በቀጥታም ኢየሱስን ያመለክታል፣ በፍጻሜ ዘመን መቼት)። አንዳንዶች የሚገምቱት እጅግ የተሻለው ታሪካዊ መቼት በዳዊት ሕይወት ላይ፣ ለእግዚአብሔር አስደናቂ፣ አስገራሚ ተስፋ፣ 2 ሳሙ. 17፡12-16 ላይ የሰጠውን ምላሽ ነው። ሌሎች ደግሞ የሚገምቱት እነዚህ የዳዊት ቃላት እንደሆኑ ነው፣ በእርጅና ዘመኑ፣ ሰሎሞን ንግሥና ከተሰጠው በኋላ። ለዚህም ምክንያቱ ዳዊት እሱን ሲጠራው፣ "ጌታዬ፣" ማለቱ ነው፣ ይኸውም እጅግ ያልተለመደ።

ለ. መዝሙራትን ለመተርጎም ሌለኛው ቁልፍ፣ ከታሪካዊ መቼት በመለስ፣ የደራሲውን ሎጂካዊ አካሄድ/ሂደት ማግኘት ነው— ለእኛ እንደ ምዕራባውያን፣ ይህ የሚከናወነው የአንቀጽ ምድቦችን ዝርዝር በማውጣት ነው። እነዚህ ጽሑፋዊ አህዶች ተመስጧዊ አይደሉም፣ ነገር ግን በቁጥሮቹ መካከል ያሉትን ሎጂካዊና ጽሑፋዊ መያያዦችን ለማግኘት እንድንችል ይረዱናል። አዲሱ የአሜሪካን መደበኛ መጽሐፍ ቅዱስ (አአመመቅ) እና አዲሱ ኢንተርናሽናል ቅጂ (አኢቅ) ይሄንን መዝሙር ወደ ቁጥር 1-3 እና 4-7 ይከፋፍሉታል። ሆኖም፣ የተከለሰው መደበኛ ትርጉም (የተመቅ) ወደ ቁጥር 1-4 እና 5-7 ይከፋፍለዋል። አዲሱ ትርጉም በአይሁድ የኅትመት ኅብረተሰብ አሜሪካ (ጀፒኤስኦኤ) ይሄንን መዝሙር ወደ ቁጥር 1 በራሱ ይከፋፍለዋል፣ ከዚያም ወደ ትይዩ ጥንዶች፡ ቁጥር 2 እና 3፤ 4 እና 5፤ 6 እና 7። ሊሆን የሚችለውም ዶ/ር ኪድነር፣ የብኪ ቲንዳሌ ተከታታይ ኮሜንተሪ፣ እጅግ የተሻለ የዚህ መዝሙር ታሳቢ መዋቅር እንዳለው ነው፡፡ እሱ የሚያስረግጠው ሁለት ጥቅሶች በእግዚአብሔር መኖራቸውን ነው፡ ቁጥር 1 እና 4። ከዚያም በእግዚአብሔር መግለጫዎች የተፈጠሩት ግጭቶች ቁጥር 2 እና 3 እና 5-7 ላይ ተገልጸዋል። መዝ. 110፡5-7 በርግጥ ከ110፡9 ጋር አይዛመድም፣ ነገር ግን ይልቁንም ከ110፡2 እና 3 ጋር ይዛመዳል እንጂ።

ሐ. አኪ ላይ መዝሙር 110ን የሚጠቅሱ ወይም ጠቃሽ የሆኑ ስፍራዎች።

1. መዝ. 110:1ሀ – ማቴ. 22:44፤ማርቆስ 12:36፤ሉቃስ 20:42፣43፤ሐዋ. 2:34፣35፤ዕብ. 1:13
2. መዝ. 110:1ለ – ማቴ. 26:64፤ሐዋ 7:55፣56፤ሮሜ. 8:34፤ኤፌ. 1:20፤ቆላ. 3:1፤ዕብ. 1:3፤8:1፤10:12፤12:2
3. መዝ. 110:1ሐ – 1 ቆሮ. 15:25፤ኤፌ. 1:22፤ዕብ. 10:13

4. መዝ. 110፡4 – ዕብ. 5፡6፤6፡20፤7፡17፡21
5. መዝ. 110፡5ሐ – ሮሜ. 2፡5፤ራዕ. 6፡17

መ. በዕብራይስጥ ሁለቱ እጅግ አስቸጋሪዎቹ ቁጥሮች መዝ. 110፡3 እና 7 ናቸው። አስደሳቹ ነገር እነርሱ ሁነኛ ስፍራ ባጠቃላይ ይሄንን መዝሙር በመተርጎም ላይ አለመያዛቸው ነው። እባክዎትን የሚገኙትን ትርጉሞች ተመልከቱ (ቃኙ) በተርጓሚዎች የተደረጉትን ሰፊ ልዩነቶች ለመገንዘብ፤ የእነዚህን አስቸጋሪዎች የዕብራይስጥ ቁጥሮች ፍሬ-ሐሳብ ለመያዝ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡110፡1-3**

**[1]እግዚአብሔር ጌታዬን፦**
**ጠላቶችህን ለእግርህ መቀመጫ እስካደርግልህ ድረስ**
**በቀኜ ተቀመጥ አለው።**
**[2]እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል**
**በጠላቶችህም መካከል ግዛ።**
**[3]ከአንተ ጋር ቀድሞ በኃይልህ ቀን፥**
**በቅዱሳን ብርሃን፥**
**ከአጥቢያ ኮከብ አስቀድሞ ከሆድ ወለድሁህ።**

**110፡1 "ጌታ አለው"** "ጌታ" የሚለው በትልልቁ ፊደላት እንደሆነ ተገንዘብ፣ ስለዚህ፣ እሱ የኪዳን ስምን የሚጠቅስ ነው፣ የእግዚአብሔርን፣ የያህዌን፣ ይኸውም ከዕብራይስጡ "የመሆን ግሥ" የሆነ (ዘጸ. 3፡14፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች)። የኪዳን አምላክ ነው እየተናገረ ያለው።

▣ **"ጌታዬን"** የጌታ ሁለተኛው ቃል ትልቁ ፊደል ያለው "ጌ" ("ጌ") ብቻ ነው፣ እና ስለዚህ፣ የዕብራይስጡን ሐዶናይ ("ጌታዬ")ን ብቻ ነው የሚያንጸባርቀው። የዕብራይስጡ ስም (ቢዲቢ 101) ፍችው "ባለቤት፣" "ባል፣" "ጌታ፣" "ጌታ" ማለት ነው። ይኸም መሲሑን መጥቀሱ ግልጽ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሲሕ)።

▣ ***"ተቀመጥ"*** ይህ ቃል "ተቀመጥ" (ቢዲቢ 442፤ ኬቢ 444፤ *ቃል ተተኳሪ*) በብዙ መንገዶች ይታያል። እሱም ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ የሚመስለው፣ የሚያመለክተው የክብር ስፍራ ነው፣ ከያህዌ ዙፋን ጎን። ያም ዐውደ-ጽሑፉ ከሆነ፣ የምንናገረው፣ ከያህዌ ጋር ስለ አብሮ ገዥነቱ ነው፣ እናም ያ እውነት ከሆነ፣ ይህ ብርቱ የመለኮት አንድምታ አለው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሥላሴ እና ልዩ ርዕስ፡ የክርስቶስ መለኮትነት ከብኪ።

"ተቀመጥ" የካህንን/የንጉሥን የተጠናቀቀ ሥራ የሚያመለክት ከሆነ፣ እሱም ወደ ዕብ. 1፡2-3፤ 10፡12-13 የተወሰደ ጠቃሽ ከሆነ፣ እንግዲያውስ "ተቀመጥ" ጠቃሽነቱ የተጠናቀቀ የመሥዋዕታዊ ሥራ እና ግዛት ነው፣ የመሲሑ/ሊቀ-ካህኑ (ዘካርያስ 3-4)።

▣ **"በቀኜ"** ይህ ሰውኛ (አንትሮፖሞርፊክ) ሐረግ ነው፣ ስለ ሰው አካል እጅግ ጠንካራ ክንድ የሚናገር። አብዛኞቹ የሰው ልጆች ባለ ቀኝ እጅ ናቸው፣ ስለዚህ ያ ክንድ ለክብር፣ ኃይል፣ ሥልጣን፣ ወይም ልዕልና ተምሳሊትነት ጥቅም ላይ ይውላል፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሲገለጽ።

▣ **"እስከ"** ይህ መስተጻምር (ቢዲቢ 723 III) ይልቁንም ችግር ያለበት ቃል ነው፣ ለእኔ፣ ምክንያቱም እሱ ማመልከት የሚሞክረው ይህ የክብር እና የሥልጣን ስፍራ በእግዚአብሔር ቀኝ፣ በጊዜ የተወሰነ ነው፣ አንዳንድ ሁነቶች እስኪሆኑ ድረስ፣ ነገር ግን እሱ ሰፊ የፍቺ መስክ አለው። የመሲሑ ግዛት ወደ አብ ግዛት ይዞራል (1 ቆሮ. 25፡24-25)።

ሆኖም፣ ይኸው ተመሳሳይ የዕብራይስጥ ተናባቢያዊ ቃል፣ በድጋሚ ሊነበብ ይችላል፣ "መቀመጫ" እንደሚለው ቃል። በዚህ መልኩ፣ "ማድረግ" ሁለት ቀጥተኛ ተሳቢዎች ወይም ተሳቢዎች አሉት፣ "መቀመጫ" እና "እግር መቀመጫ።" ከአሦራውያን የግድግዳ ስዕሎችና ጽሑፎች እንደምንረዳው ዙፋንና የንጉሥ ጠረጴዛ የሚያርፈው በባሮች ጀርባ ላይ ነው፣ ያም የዚህ ሐረግ ጠቃሽ ሊሆን ይችላል፣ መዝ. 110፡1 ላይ።

▣ **"የእግር መቀመጫ"** እንደገና፣ ይኸም ግልጽ የሆነ ጥንታዊ የምስራቅ ዘይቤ ነው፣ ለድል በጠላቶች ላይ (ኢያ. 10፡24)።

**110፡2 "እግዚአብሔር የኃይልን በትር ከጽዮን ይልክልሃል"** ይሄንን ቁጥር ለመተርጎም በርካታ መንገዶች አሉ፣ ነገር ግን እየተናገርን ያለነው ስለ ያህዌ ሁለንተናዊ አገዛዝ መሆኑ ግልጽ ነው፣ ከኢየሩሳሌም ዙሪያ ማዕከል ተነሥቶ መላውን ዓለም ለማካለል። በርካታ የብኪ ጠቃሾች አሉ፣ ለዚህ ሁነት። ይህም የመሲሑን ግዛት የሚናገር ይመስላል፣ እንደ ያህዌ ተወካይ።

"በትር" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 641) በዋነኛነት የሚጠቅሰው ከእንጨት የተሠራን ነገር ነው።

1. የጦርነት ዱላ
2. የበግ እረኝነት በትር

እሱም የገዥነትና የሥልጣን ተምሳሊት ነው። በያህዌ ግዛት ዐውደ-ጽሑፍ ላይ፣ አሁንም የያህዌን ሥልጣንና ኃይልን ያመለክታል፣ በተወካይ መሪ በኩል (ማለትም፣ የሙሴ በትር፣ ዘጸአት 4፤ 7)።

▣ **"በጠላቶችህም መካከል ግዛ።"** "መግዛት" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 921 I፤ ኬቢ 1190፤ *ቃል ተተኳሪ*) እጅግ ብርቱ ቃል ነው (ማለትም፣ "ገዥነት፣" ዳን. 7፡13-14)። ይህም ከመዝሙር 2 ጋር ተመሳሳይ ነው፣ (በተለይም መዝ. 2፡9)። መዝሙር 2 ከመዝሙር 110 ጋር ብዙ የሚጋራው አለው።

1. ሁለቱም ያህዌንና መሲሑን ያካትታሉ

2. ሁለቱም ከዓለም ግዛቶች (ኢምፓየርስ) ጋር የሚደረገውን ውጊያ ያካትታሉ

**110፡3 "ሕዝብህ በፍቃደኝነትና በነጻነት ይሆናሉ በሥልጣን በሆንክበት ጊዜ"** መሲሑ በጠላቶቹ ላይ እንዴት እንደሚያደርግ እና የመሲሑ ሕዝቦችም በጉዳዩ ላይ እንዴት እንደሚሰባሰቡ ያለውን ተቃርኖ ተገንዘብ። ይህም ከፍቃደኛው ሠራዊት ጋር ይመሳሰላል መሳ. 5፡2 ላይ ካለው ጋር። ይህ ሐረግ፣ "በፍቃደኝነትና በነጻነት፣" በቀዳሚነት ጥቅም ላይ ይውል የነበረው ለነጻ ፍቃድ ስጦታ ነበር።

1. የማደሪያውን ድንኳን ወይም ኋላ ላይ መቅደሱን ለመገንባት
2. በመቅደስ የሚሆን መሥዋዕት

ይህ የሮሜ 12፡1 ጠቃሽ ሊሆን ይችላል፣ አማኞች ሰውነታቸውን ሕያው መሥዋዕት አድርገው ለእግዚአብሔር የሚሰጡበት። ይህ የተዋበ ስዕል ነው፣ የእግዚአብሔር ለመሲሑ መስጠት።

ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 393) የሚለው የአናባቢዎች ለውጥ መደረጉን ነው

1. "የአለቅነት ስጦታ ተሰጠህ" — አአመቅ
2. "ለሕዝብህ ማደርያ አደረግህ" — የተእመቅ

ሆኖም፣ ዩቢኤስ ለአማራጩ "ሐ" ደረጃ ብቻ ነው የሚሰጠው (ምክንያታዊ ጥርጣሬ)። ጄፒኤስኦኤ ሐረጉን የሚተረጉመው "ሕዝብህ በፍቃዳቸው ወደ ፊት ይመጣሉ፣ በውጊያህ ቀን፣" እሱም ኤምቲን የሚከተል።

▣ **"በተቀደሰ የሰልፍ ሥርዓት"** ሁለት ዓይነት የተለያዩ መንገዶች አሉ ይሄንን ቁጥር ለመመልከት። "ቅዱስ የሰልፍ ሥርዓት" ማሶረቲክ ቴክስትን (ጽሑፍ) (ኤምቲን) እና ሴፕቱዋጂንትን (LXX) ተከትሎ የመጣ ነው። ሆኖም፣ አንዳንድ ትርጉሞች የዕብራይስጡን "ዲ" ወደ "አር" ይቀይሩታል እናም "የቅድስና ተራራዎች" በሚል ይተረጉሙታል፣ ይህንንም የሲማቹስ ትርጉም ይከተለዋል፣ የዕብራይስጥ፣ ጄሮም ትርጉም፣ እና የተመቅ። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 394) ለዚህ አማራጭ "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል፣ (ምክንያታዊ ጥርጣሬ)።

▣ **"የአጥቢያ ማኅፀን"** ይህ ገለጻ ስለ ምን ለመሆኑ ርግጠኝነት የለውም

1. መሲሑ ራሱ
2. የእርሱ ሠራዊት
3. የበረከትና የዘላለማዊነት ዘይቤ

ጤዛ አጥቢያ ላይ በየጠዋቱ እንደሚመጣ፣ በዚህ በተትረፈረፈ መልኩ፣ በፍልስጥኤም አካባቢዎች፣ ብዙዎቹ ተንታኞች የሚያስረግጡት ይህ የበረከት (መትረፍረፍ) ዘይቤ እንደሆነ ነው።

ይህ አስቸጋሪ ቁጥር ነው።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ጉብዝናህ"** |
| **አኪጀቅ፣ አኢመቅ፣ የተእመቅ** | **"የጉብዝናህ"** |
| **አየተመቅ** | **"ጉብዝናህ ወደ አንተ ይመጣል"** |
| **ጄፒኤስኦኤ** | **"ጉብዝና"** |
| **LXX** | **"ወለድሁህ"** |

ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 396) የሚለው የአናባቢዎች ለውጥ መደረጉን ነው፣ በውጤቱም "እኔ ወለድሁህ" (LXX፣ ፔሺታ፣ ቫልጌት፤ ኒዶቲ ተመልከት፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 124፣ ቁ. 11)፣ ነገር ግን "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል (ምክንያታዊ ጥርጣሬ)፣ ሆኖም ከኤምቲ በተሻለ ይመርጠዋል። LXX יְלִדְתִּיךָ ይወስዳል እንደ ግሡ ቅርጽ יָלַד (ቢዲቢ 408) "መውለድ" ወይም "ማምጣት።" "ጎበዝ" ከዚህ ግሥ የመጣ ነው፣ יַלְדוּת (ኒዶቲ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 455)።

## መዝሙር ፡110፡4-7

**4እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት**
**አንተ ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ፥**
**እግዚአብሔር ማለ አይጸጸትም።**
**5እግዚአብሔር በቀኝህ**
**ነገሥታትን በቍጣው ቀን ይቀጠቅጣቸዋል።**
**6በአሕዛብ መካከል ይፈርዳል፥**
**ሬሳዎችንም ያበዛል**
**በሰፊ ምድር ላይ ራሶችን ይቀጠቅጣል።**
**7በመንገድ ከፈሳሽ ውኃ ይጠጣል**
**ስለዚህ ራስ ከፍ ከፍ ይላል።**

**110፡4 "እግዚአብሔር ማለ"** ግሡ (ቢዲቢ 989፣ ኬቢ 1396) ኒፋል የተጠናቀቀ ነው። ይህ እጅግ ብርቱ የሆነ የማስረገጫ መንገድ ነው፣ እግዚአብሔር የሚለው እውነት ለመሆኑና ዘወትርም እውነት እንደሚሆን! እባክዎን ዕብ. 6፡16-18 ያንብቡ፣ እዚያም እግዚአብሔር ሁለት የማይቀየሩ ነገሮችን ያለበት፣ የእርሱን ተስፋዎችና የእርሱን መሐላ። መሠረታዊ መታመኛችን የእግዚአብሔር ታማኝነት ነው፤ እርሱ ሲናገርና ቃል ሲገባ፣ ያለው የታመነ ነው።

"ምሏል" መዝ. 110፡4 ላይ ትይዩነቱ "ብሏል" ነው፣ 110፡1 ላይ።

▣ **“ሐሳቡን አይቀይርም”** ይኽም ሌላው ሰዋዊ ሐረግ ነው (“መጸጸት፣” ቢዲቢ. 636፣ ኬቢ. 688፣ *ኒፉል ያልተጠናቀቀ*) የሰውን መጸጸት ወይም መለዘብ በተመሳሳይነት በመጠቀም፣ እግዚአብሔር የማያደርገውን ለመግለጽ ነው (ዕብ. 7፡21)።

ባለቤቱ ያህዌ መሆኑ ግልጽ ነው። አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ሌሎቹ ተውላጠ ስሞች፣ የመዝ. 110፡5-7 የሚያመለክቱት ድል አድራጊውን፣ ብርቱውን ያህዌን ወይም የእርሱን ምድራዊ ተወካይ ነው (ማለትም፣ የእርሱ የኪዳን ሕዝቦች ንጉሥ)።

▣ **“እንደ መልከ ጼዴቅ ሥርዓት**

**አንተ ለዘላለም ካህን ነህ”** የአይሁድ የኅትመት ኅብረተሰብ የአሜሪካ (ጄፒኤስኦኤ) ይህንን የሚተረጉመው፣ “አንተ ለዘላለም ካህን ነህ፣ ጻድቅ ንጉሥ በእኔ ሥርዓት።” የ“መልከ ጼዴቅ ሥርዓት”ን በብዙ መንገዶች መረዳት ይቻላል።

1. የእርሱ ስም ፍችው፣ “የጽድቅ ንጉሥ”
2. የእርሱ ከተማ ትታያለች፣ ማለትም፣ ኢየሩሳሌም
3. እርሱ ብቸኛው ሰው ነው ብኪ ላይ፣ ሁለቱንም የሆነ፣ ንጉሥና ካህን

የአኪ የመልከ ጼዴቅ ማብራሪያ ዕብራውያን ላይ ይገኛል (ዕብ. 5፡6፤10፤6፡20፤7፡1፣10፣11፣15፣17)። የብኪ ገለጻ የሚገኘው ዘፍ. 14፡18-20 ላይ ነው። መልከ ጼዴቅ ጥቅም ላይ የዋለው አብርሃም አስራትን ስለከፈለው ነው (ማለትም፣ ዘፍ. 14፡20)፣ ስለዚህ፣ በአይሁድ አገባብ መሠረት፣ እሱ የላቀ ክህነት አለው፣ ከአይሁድ ክህነት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መልከ ጼዴቅ)።

1. እሱ ከቁልፍ (ዋና) ከተማ ነበር
2. እሱ ተገቢ ስም አለው
3. እሱ ተገቢ አቋም ይዟል፡ ካህን/ንጉሥ

▣ “ዘላለም” የሚለውን ቃል አጠቃቀም ተገንዘብ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም ([‘ኦላም])። ይህም የሚያመለክተው የፍጻሜ ዘመን መቼትን፣ ግለሰብን፣ እና ድልን ነው! አኪ ተመስጧዊ ከሆነ፣ (ነውም!)፣ ይህ መዝሙር የሚያመለክተው በተለይ የናዝሬቱ ኢየሱስን ነው!

**110፡5 “እግዚአብሔር በቀኝህ ነው”** ይህ የተለየ ምናብ ነው ከመዝ. 110፡1ለ። እንደሚመስለኝ ምንም ዓይነት ርግጠኛ ሥነ-መለኮታዊ ጠቀሜታ የለውም፣ ልዩነቱ ላይ። እሱ እንዲያው የሚለው መሲሑ ኃይልን እንደሚታጠቅ፣ እንደሚደገፍ፣ እና እንደሚበረታታ ነው፣ በያህዌ በራሱ (መዝ. 110፡4)።

**110፡5፣ 6ሐ “ነገሥታትን በቍጣው ቀን ይቀጠቅጣቸዋል።”** ነገሥታት እዚህጋ ጥቅም ላይ የዋሉት የያህዌን ድል መጥቀሻ መንገድ ነው፣ ፣ በአሕዛብ ሠራዊት ላይ (“ነገሥታት፣ 110፡5፤ “አሕዛብ፣” 110፡6፤ “አለቆች፣” 110፡7 የሚያመለክቱት ሁለንተናዊ ምናባዊነትን (ምስያ) ነው፤ አየተመት “ሰፊ ምድር” የሚል አለው 110፡6ሐ ላይ)። ይኸው ተመሳሳይ የፍጻሜ ዘመን ግጥሚያ መዝሙር 2 እና ራዕይ 19፡11-21 ላይ ይታያል።

**110፡6 “በአሕዛብ መካከል ይፈርዳል፥”** ይኽም የፍጻሜ ዘመንን መቼት ይጠቅሳል። እንደገና፣ እግዚአብሔር ነው ከመላው ዓለም ጋር የሚሠራው፣ በሁለቱም በፍርድ እና፣ በእርሱ በኩል በአንድምታ የተመለከተው፣ ግን ያልተቀመጠው፣ በምሕረት።

**110፡7** ይህ ቁጥር በዕብራይስጥ አስቸጋሪ ነው፣ እጅግ አስቸጋሪነቱ አንዳንድ ሊቃውንት የሚያስረግጡት የጽሑፉን ከፊል እንዳጣነው ነው። ምንም ዓይነት ትክክለኛ ፍች ይኑረው፣ እሱ የድል ተምሳሌት መሆኑ ግልጽ ነው (ማለትም፣ እግዚአብሔር የሚቃወሙትን ሁሉ አሸንፏል)። ዘይቤው የተቀዳ የሚመስለው ከሚሸሽ፣ ከተሸነፈ ጠላት ነው፣ አሳዳጁ ባለ ድልም በውኃ ማቋረጫ ላይ ዘና ለማለት ጊዜ ይኖረዋል፣ ስለዚህ፣ ኃይሉን ያድሳል። ሌላው ታሳቢ ትርጉም፣ “ራስን ቀና ማድረግ፣” መዝ. 3፡3 እና 27፡6 ላይ ይገኛል፣ እዚያም የእግዚአብሔር መሲሕ ነው እንደ ጻድቅ ፈራጅ እሱም የሕዝቡን ራስ ቀና የሚያደርግ፣ ለእነርሱ እውቅና በመስጠት። የትኛውንም ዓይነት ጠቃሽ ቢሆን፣ (1) የመሲሑ ብርታትና ሰውነት ወይም (2) የምሕረት ድርጊት ለገዛ ሕዝቡ፣ ተቃዋሚዎችን ሁሉ ድል በማድረግ፣ ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ ርግጠኝነት የለውም።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ሁለቱም ኢየሱስም ሆነ የእርሱ ሐዋርያት ይሄንን መዝሙር ከሌሎቹ ይልቅ ለምን ጠቀሱ?
2. በእግዚአብሔር በቀጥታ መጠቀሱ መዝ. 110፡1 እና 4 ጠቀሜታው ምንድነው?
3. በዚህ መዝሙር ላይ መሲሑን እንደ ነቢይ፣ ካህን፣ እና ንጉሥ የሚጠቅሰውን የቱጋ ነው የምናገኘው?
4. ብዙ የተለያዩ ትርጉሞች መዝ. 110፡3 እና 7 ላይ መኖራቸው ለምንድነው?

# መዝሙር 111

## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ ስለ መልካምነቱ ተመሰገነ<br><br><u>ኤምቲ መግቢያ የለውም</u> | ምስጋና ለእግዚአብሔር ስለ ታማኝነቱና ፍርዱ | ውዳሴ ምስጋና ለጌታ ስለ ታላቅ ሥራው | ጌታን ስለ ማመስገን | የያህዌን ሥራ ማመስገን |
| 111:1-6 | 111:1 | 111:1-10 | 111:1ሀ | 111:1ሀ |
| | | | 111:1ለ-3 | 111:1ለ-2 |
| | 111:2-6 | | | |
| | | | | 111:3-4 |
| | | | 111:4-6 | |
| | | | | 111:5-6 |
| 111:7-10 | 111:7-9 | | 111:7-10 | 111:7-8 |
| | | | | 111:9-10 |
| | 111:10 | | | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መዝሙር 111 እና 112 መስቀልያ፣ የጥበብ መዝሙሮች ናቸው። እያንዳንዱ የቅኔ ስንኝ (መስመር) የሚጀምረው በቀጣዩ ፊደል ነው፣ በዕብራይስጥ የፊደል ገበታ። መስቀልያው መዝ. 111፡1ለ ላይ ይጀምራል።

ለ. እነዚህ ሁለት መዝሙሮች ደግሞ፣ "ምሕረቱ ለዘላለም ነውና፣" በሚለው ሐረግ ይተሳሰራሉ፣ እሱም መዝሙር ላይ ብቻ የሚከሰት፣ መዝ. 111፡3 እና መዝ. 112፡3፣9 ላይ።

ሐ. መዝሙር 111 ያህዌን ያመሰግናል፣ መዝሙር 112 ደግሞ የያህዌን ታማኝ ተከታዮች ሲያመሰግን።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡111፡1-6**

[1]ሃሌ ሉያ።
አቤቱ፥ በቅኖች ሸንጎ በጉባኤም
በፍጹም ልቤ አመሰግንሃለሁ።
[2]የእግዚአብሔር ሥራ ታላቅ ናት፥
ደስ በሚሰኙባት ሁሉ ዘንድ የተፈለገች ናት።
[3]ሥራው ምስጋናና ግርማ ነው
ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል።
[4]ለተአምራቱ መታሰቢያን አደረገ
እግዚአብሔር መሓሪና ይቅር ባይ ነው።

[5]ለሚፈሩት ምግብን ሰጣቸው
ኪዳኑንም ለዘላለም ያስባል።
[6]የአሕዛብን ርስት ይሰጣቸው ዘንድ
ለሕዝቡ የሥራውን ብርታት አሳየ።

**111:1 "ሃሌ ሉያ"** ይህ የዕብራይስጡ ቃል "ሃሌ ሉያ" ትርጉም ነው። እሱም "አመስግኑ" ከሚለው ግሥ (ቢዲቢ 237 II፣ ኬቢ 248፣ ፒል ተተኳሪ) እና "ያህ" ከሚለው የተሠራ ነው (ቢዲቢ 219)። እሱም የአምልኮ መቼትን ይገልጻል፣ እናም ከአምልኮ ደንብ አኳያ ጥቅም ላይ የሚውለው በመጀመሪያ ወይም በመጨረሻ ላይ ነው፣ በብዙ መዝሙሮች ላይ (ማለትም፣ መዝ. 102:18፤104:35፤105:45፤106:1፣48፤111:1፤112:1፤113:1፣9፤ 115:17፣18፤116:19 እና ተጨማሪ ሃያ አንድ ጊዜያት)።

የአምልኮ ደንብ ገጽታው መዝ. 111:1ሐ ላይ ተረጋግጧል።

የመጀመሪያው ስንኝ (መስመር) የመስቀልያው ክፍል አይደለም ነገር ግን ለዚህ መዝሙር ርዕስ ሆኖ ያገለግላል።

▣ **"ጌታ"** ይህ የእስራኤል አምላክ የኪዳን ስም ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ **"እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ"** ከስንኝ 1 ጋር ያለውን ትይዩነት ተገንዘብ፣ የተለያዩ መልኮች ግን ተመሳሳይ ጽንሰ-ሐሳብ።

1. ሃሌ ሉያ – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ፒል ተተኳሪ
2. አመሰግናለሁ – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

▣ **"በፍጹም ልቤ"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ለፍጹም መሰጠት (መዝ. 9:1፤86:12፤138:1)። ለ "ልብ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ።

▣ **"በቅኖች ሸንጎ በጉባኤም"** ይህ ሐረግ የሚያመለክተው

1. የአንድ ወገን (ቡድን) ምዕመናን (አምላኪዎች)ን ነው፣ በመቅደስ
2. ሁለት ወገኖችን (ቡድኖች) (መዝ. 107፡32)
   ሀ. የተወሰኑ መሪዎችን (ዘጸ. 3፡16)
   ለ. ትልቅ የምዕመናን ቡድን

**111:2-6** ትይዩውን ተመልከት፣ በመካከል ያለውን

1. የእግዚአብሔር ሥራ ታላቅ ነው፣ መዝ. 111፡2ሀ
2. ሥራው ድንቅና ባለ ግርማ ነው፣ መዝ. 111:3ሀ (መዝ. 96:6፤104:1)
3. ተአምራቱ መታሰቢያ አላቸው፣ መዝ. 111፡4ሀ
4. ለሕዝቡ የሥራውን ብርታት አሳየ፣ መዝ. 111፡6ሀ

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተአምራት (አስደናቂ ነገሮች) ያህዌ ራሱን የሚገልጽበት የተለያዩ መንገዶችን ለመመልከት፣ በሥራዎቹና በቃሉ።

**111:2ለ** እንደ መምህር/ሰባኪ፣ ሐረጉ ለእኔ በብርቱ ነው የሚናገረኝ "የእግዚአብሔር መገለጥ ለሁሉም ይገኛል፣ ነገር ግን መጠናት/በጥልቀት መሰላሰል እና መተግበር ይኖርበታል" (መዝ. 111፡10ለ፤ እዝራ 7፡10)! በእነርሱ ትደሰታላችሁን፣ ትኖሩባቸኋልን፣ ታስተምራቸኋልን?

**111:3ለ "ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል።"** ይህ ሐረግ መዝ. 112፡3፣9 ላይ ተደግሟል፣ እናም የትም ሌላ ስፍራ አይገኝም በእነዚህ ተመሳሳይ ቃላት። ይህም አንድምታው መዝሙር 111 እና 112 በአንድ ሰው እንደተጻፉ ነው።

ለያህዌ ጽድቅ ተደጋጋሚ ጽንሰ-ሐሳብ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ።

"ይኖራል" የሚለው አንቀጽ (ቢዲቢ 763፣ ኬቢ 840) ደግሞ ለእግዚአብሔር መገለጥ (ራዕይ) ጥቅም ላይ ውሏል፣ መዝ. 19፡9 ላይ። ኢየሱስ የብኪን ተመስጧዊነትና ዘላለማዊነት ማቴ. 5፡17-19 ላይ ገልጿል!

**111:4ለ** በእግዚአብሔር ከማመን በኋላ ከዋነኞቹ ጥያቄዎች በኋላ አንደኛው፣ እሱ ምን ይመስላል ነው። ባሕርዩ ምንድነው? ይህ ሐረግ የእስራኤልን አምላክ የብኪ ባሕርይ ያንጸባርቃል (ዘጸ. 34:6-7፤ዘኍ. 14:18፤ዘዳ. 4:31፤ነህ. 9:17፤መዝ. 86:15፤103:8፤145:8)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት።

**111:5-6** እነዚህ ቁጥሮች እግዚአብሔር ያደረገውን አንዳንድ ነገሮች ይገልጻሉ።

1. ለሚፈሩት/ለሚያከብሩት ምግባቸውን ይሰጣል (ማለትም፣ ዘጸአት እና ዘኁልቍ፤ ማቴ. 6፡11፣31-33)
2. ኪዳኑን ለዘላለም ያስባል (ማለትም፣ ይህ የሚያመለክተው ለአባቶች የሰጠውን ተስፋ ነው፣ ዘፍጥረት 12፤ 15፤18፤22፤መዝ. 105:8፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን)
3. ለሕዝቡ ራሱን አሳየ (አሳወቀ) (መዝ. 19፡7-12)
4. አሕዛብን ለሕዝቡ ርስት አድርጎ ይሰጣል
   ሀ. በመሲሐዊ መልኩ፣ መዝ. 2፡8፤ 67፡7 ላይ
   ለ. ከነአንን ድል በማድረግ መልኩ፣ ዘፍ. 15፡12-21 ላይ

**መዝሙር ፡111፡7-10**

[7]የእጆቹ ሥራ እውነትና ፍርድ ነው
ትእዛዙም ሁሉ የታመነ ነው፥

[8]ለዘላለምም የጸና ነው፥
በእውነትና በቅንም የተሠራ ነው።
[9]መድኃኒትንም ለሕዝቡ ሰደደ፥
ኪዳኑንም ለዘላለም አዘዘ
ስሙ የተቀደሰና የተፈራ ነው።
[10]የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፥
ለሚያደርጓትም ሁሉ ደኅና ማስተዋል አላቸው
ምስጋናውም ለዘላለም ይኖራል።

**111፡7-10** ይህ አንጓ የእግዚአብሔርንና የእርሱን ራዕይ/ተስፋ ታማኝነት ያስረግጣል። እሱም ለመዝሙር 119 ጥላ (ንግር) የሆነ እና መዝሙር 19ን የሚያንጸባርቅ ነው።

የእግዚአብሔር ራዕይ የሚገለጽባቸውን መንገዶች ተገንዘብ።

1. እውነትና ፍርድ (መዝ. 19፡9)
2. የታመነ (መዝ. 19:7፤93:5)
3. ለዘላለም የጸና ነው (መዝ. 19:9)
4. በእውነትና በቅንም የተሠራ ነው

እግዚአብሔር ራሱ የተገለጸበትን መንገድ ተገንዘብ።

1. ለሕዝቡ መድኃኒትን ላከ
2. ኪዳኑንም ለዘላለም አዘዘ
3. እሱ የተቀደሰና የተፈራ ነው

የእርሱን መገለጥ ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋሉትን የተለያዩ ቃላት ተገንዘብ።

1. ሐሳቡ – ቢ.ዲ.ቢ. 824 (መዝ. 19:8)
2. ትእዛዙ – ቢ.ዲ.ቢ. 845 (መዝ. 19:8፤ስም በመጠቀም፣ ቢ.ዲ.ቢ. 846)
3. ፍርሃት – ቢ.ዲ.ቢ. 432 (መዝ. 19:9)

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ለእግዚአብሔር ራዕይ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት።

**111፡7 "እጆቹ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሲገለጽ (ሰውኛ/አንትሮፖሞርፊዝም)።

▣ **"እውነት"** ይህ አንስታይ (የሴት) ስም (ቢ.ዲ.ቢ. 54) መዝ. 111:7 እና 8 ላይ ይታያል። እሱም በጥሬው "ታማኝነት" ማለት ነው። ተመሳሳይ የዕብራይስጥ ሥር (ቢ.ዲ.ቢ. 54) "የታመነ" የሚል ቃል ይፈጥራል (ቢ.ዲ.ቢ. 52፣ ኒፋል አንቀጽ) መዝ. 111:7 (መዝ. 19:7) ላይ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ።

**111፡8 "ከዘላለም እስከ ዘላለም"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ አቀራረብ የተዋቀረው በ

1. ዘላለም – ቢ.ዲ.ቢ. 723 I (መዝ. 111:3፣8፤112:3፣9)
2. እስከ ዘላለም – ቢ.ዲ.ቢ. 761 (መዝ. 111:9፤19:9፤ልዩ ርዕስ ተመልከት: ዘላለም [ኦላም])

**111፡9 "መዋጀት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መዋጀት/መቤዠት

▣ **"ቅዱስ"** "ቅዱስ" (ቢ.ዲ.ቢ. 872) እና "የተፈራ" (ቢ.ዲ.ቢ. 431) አንድ ላይ መዝ. 99:3 ላይ ይከሰታሉ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቅዱስ።

▣ **"የተፈራ"** ይህ የተለመደ የዕብራይስጥ ግሥ ነው፣ ለ"ለመፍራት" (ቢ.ዲ.ቢ. 431፣ ኬቢ. 432፣ ኒፋል አንቀጽ)። እሱም ጥቅም ላይ የሚውለው

1. ለያህዌ ለራሱ – ዘዳ. 7:21፤10:17፣21፤መሀ. 1:5፤4:14፤9:32፤መዝ. 47:2፤68:35፣76:7፤ዳን. 9:4
2. ለእርሱ ድርጊቶች – መዝ. 65:5፤66:3፣5፤106:22፤145:6
3. ለሕዝቡ ተገቢ ምላሽ – ዘዳ. 4:10፤5:5፤6:2፣13፣24፤10:12፣20፤13:11፤14:23፤17:13፣19፤19:20፤21:21፤25:18፤28:58፤31:12፤ኢያ. 4:24
4. ለአሕዛብ – ዘዳ. 28:10፤ኢያ. 4:24፤9:24፤መዝ. 67:7

**111፡10ሀ** ይህ ቀዳሚው መርሕ እና ማዕከላዊ ጭብጥ ነው፣ የምሳሌ (ምሳ. 1:7፤9:10)፣ ደግሞም ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ተመልከት መክ. 12:13 ላይ።

**111፡10ለ** የእግዚአብሔርን ራዕይ ማወቅ እሱን/እነርሱን መታዘዝን እንደሚጠይቅ ተገንዘብ! መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ሥነ-መለኮታዊ ዶክትሪን ብቻ አይደለም፣ ለማረጋገጥ፣ የሕይወት ስልት እንጂ (ማቴ. 7:13-27፤ኤፌ. 2:8-9፣10)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝ. ııı፡ıሐ ላይ የተመለከተው "ሸንጎ" ምንድነው?
2. መዝሙሩ በትክክል የትኞቹ "የጌታ ሥራዎች" እንደሚመሰገኑ (እንደሚከብሩ) ይነግረናልን?
3. መዝ. ııı፡4ለ ከዘጸ. 34፡6-7 እንዴት ይዛመዳል?

# መዝሙር 112
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው ብልጽግና | የጻድቅ የበረከት አቋም | ተቃራኒነት ያለው የጻድቅ እና የኃጢአተኛ ዕጣ | የደግ ሰው ደስታ | የቅን ሰው ምስጋና |
| | | (የጥበብ መዝሙር) | | |
| ኤምቲ መግቢያ የለውም | | | | |
| 112:1-6 | 112:1ሀ | 112:1-3 | 112:1ሀ | 112:1ሀ |
| | 112:1ለ-መ | | 112:1ለ-3 | 112:1ለ-2 |
| | 112:2-8 | | | |
| | | | | 112:3-4 |
| | | 112:4-10 | 112:4-6 | |
| | | | | 112:5-6 |
| 112:7-9 | | | 112:7-10 | 112:7-8 |
| | 112:9-10 | | | 112:9 |
| 112:10 | | | | 112:10 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

*ሀ.* የመዝሙር 111ን ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ግልጽ ለሆነው በመዝሙር 111 እና 112 መካከል ላለው ግንኙነት።

*ለ.* መዝሙር 111 ያህዌን ያመሰግናል መዝሙር 112 ግን ታማኝ ተከታይን ያመሰግናል (መዝሙር 128)።
1. እግዚአብሔርን ይፈራል፣ መዝ. 112፡1ለ
2. ትእዛዙንም ይወድዳል፣ መዝ. 112:1ሐ (መዝ. 1:2)
3. ዘሩ በምድር ላይ ኃያል ይሆናል፣ መዝ. 112:2ሀ
4. እነርሱም ይባረካሉ፣ መዝ. 112:2ለ
5. እነርሱ ባለጠጎች ይሆናሉ፣ መዝ. 112:3ሀ
6. ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል፣ መዝ. 112:3ለ
7. እሱና ቤተሰቡ በጨለማ ብርሃን ይወጣላቸዋል፣ መዝ. 112:4ሀ
8. መሐሪ ነው፣ መዝ. 112:4ለ፣ 5ሀ፣ 9ሀ
9. ሩኅሩኅ ነው፣ መዝ. 112:4ለ
10. እሱ ቅን ነው፣ መዝ. 112:4ለ
11. በፍርድም መኮንኖቹን ይዳኛል፣ መዝ. 112:5ለ
12. ፈጽሞ አይናወጥም፣ መዝ. 112:6ለ
13. የእሱና የቤተሰቡ የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል፣ መዝ. 112:6ለ
14. ከክፉ ነገር አይፈራም፣ መዝ. 112:7ለ
15. ልቡ ጽኑ ነው (መዝ. 57:8፤108:1)፣ በእግዚአብሔር ይታመናል፣ መዝ. 112:7ለ (ኢሳ. 26:3)
16. ልቡ የጸና ነው፣ ቢዲቢ 701፣ ኬቢ 759፣ *ቃል* PASSIVE አንቀጽ (ማለትም፣ በእግዚአብሔር)፣ መዝ. 112:8ሀ

17. አይፈራም፣ መዝ. 112:8ሀ
18. ጠላቶቹም በፊቱ ይሸነፋሉ፣ መዝ. 112:8ለ፣ 10ሀ
19. ጽድቁ ለዘላለም ይኖራል፣ መዝ. 112:9ለ
20. ቀንዱም በክብር ከፍ ከፍ ይላል፣ መዝ. 112:9ሐ (መዝ. 75:10)

ሐ. በተቃራኒው ኃጢአተኞች ትክክለኛ ተቃራኒው ይገጥማቸዋል። የእነርሱም ዕጣ ተለይቶ ተጠቅሷል፣ መዝ. 112፡10 ላይ።
1. ኃጢአተኞች የጻድቅን መባረክ ይመለከታሉ፣ እናም ይቸገራሉ
2. ጥርሳቸውን ያፋጫሉ
3. ቀልጠው ይጠፋሉ
4. ፍላጎታቸውም ይጠፋል

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡112፡1-6**

**[1]ሃሌ ሉያ።**
**እግዚአብሔርን የሚፈራ፥**
**ትእዛዙንም እጅግ የሚወድድ ሰው ምስጉን ነው።**
**[2]ዘሩ በምድር ላይ ኃያል ይሆናል**
**የቅኖች ትውልድ ትባረካለች።**
**[3]ክብርና ባለጠግነት በቤቱ ነው፥**
**ጽድቁም ለዘላለም ይኖራል።**
**[4]ለቅኖች ብርሃን በጨለማ ወጣ**
**መሓሪና ይቅር ባይ ጻድቅም ነው።**
**[5]ቸር ሰው ይራራል ያበድራልም፥**
**በፍርድም ነገሩን ይፈጽማል።**
**[6]ለዘላለም አይናወጥም**
**የጻድቅ መታሰቢያ ለዘላለም ይኖራል።**

**112፡1 "ሃሌ ሉያ"** መዝ. 111፡1 ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"እንዴት ምስጉን ሰው ነው..."** ይህ የጥበብ ቃል ነው።
1. የተባረከ (አእቅ፣ "ደስታ")፣ መዝ. 112:1 – ቢዲቢ 80 (መዝ. 1:1፤119:1-2)
2. የተባረከ፣ መዝ. 112:2 – ቢዲቢ 138
3. መልካም (አእቅ፣ "ደስታ")፣ መዝ. 112:5 – ቢዲቢ 373 II

▣ **"እግዚአብሔርን የሚፈራ"** ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 111፡10 ላይ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መፍራት።

▣ **"ትእዛዙንም እጅግ የሚወድድ ሰው"** ግሡ (ቢዲቢ 342፣ ኬቢ 339፣ ቃል የተጠናቀቀ) የሚገልጸው የግለሰቡን አዝማሚያ ነው፣ ለያህዌ መገለጥ (ትእዛዝ) (መዝ. 19:10፤111:2፤119:35)። ታማኝ ተከታይ እነርሱን ያከብራቸዋል (ዘዳ. 4:1-2፣14፣40፤16:12፤30:8፣16፣19-20)።
ለ "ትእዛዛት" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ።

**112፡2** ከአስርቱ ትእዛዛት የምንማረው ክፉ በትውልድ መካከል እንደሚንቀሳቀስ ነው (ዘጸ. 20:5፤ዘዳ. 5:9፣10) ነገር ግን፣ እግዚአብሔር ይመስገን፣ እምነትም እንዲሁ ያደርጋል (ዘጸ. 20:6፤ዘዳ. 5:10፤7:9፤ዘጸ. 34:7)።

**112:3ሀ** ይህ የብኪ ጽሑፍ መሆኑን አስታውስ፣ የሙሴ ኪዳን "ሁለቱ መንገዶች" (ዘዳ. 30:15-20፤መዝሙር 1፤ ምሳ. 4:10-19፤ኤር. 21:8፤ማቴ. 7:13-14)። ይህ አልሠራም፣ ከሰው ልጅ የወደቀ ተፈጥሮ የተነሣ (ዘፍጥረት 3፤ ሮሜ 1-3፤ ገላትያ 3፤ ዕብራውያን)። ለእነዚህ ቁጥሮች አቃቂር ከማውጣት ተጠንቀቅ፣ በብልጽግና ላይ፣ እነርሱ የአኪ ተስፋዎች እንደሆኑ ሁሉ!

**112፡4ሀ** ይህ ሐረግ አንድምታው ታማኝ ተከታይ በዚህ በወደቀው ዓለም በመከራ መሐል እንኳ ግንዛቤ እንዳለው ነው፣ ምክንያቱም
1. እግዚአብሔርን ስለሚፈራ፣ መዝ. 112:1ለ፣7ለ
2. ትእዛዙን ይወድዳል፣ መዝ. 112:1ሐ
3. በእምነት ይኖራል፣ መዝ. 112:4ለ-5
4. አይናወጥም፣ መዝ. 112:6ሀ
5. አይፈራም፣ መዝ. 112:8ሀ

▣ "ይነሣል" የሚለው ግሥ ባለቤት (ቢዲቢ 280፣ ኬቢ 281፣ ቃል የተጠናቀቀ) ተለይቶ የተቀመጠ አይደለም። እሱ ታማኝ ተከታይን የሚጠቅስ ሊሆን ይችላል። ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 960) የሚለው "እሱ በጨለማ እንደ ብርሃን ነው፣ ለከበሩ ሰዎች እንደሚያበራ (ማለትም፣ ቅን፣ ተባዕታይ (ወንዶ) የብዙ ቁጥር።"

**112፡4ለ** እነዚህ ተመሳሳይ አስተዋጽዖዎች የተባሉት ለያህዌ ነው፣ መዝ. 111:3ለ፣4ለ (ዘጸ. 34:6-7 ላይ)። ይህ የቅኔ ስንኝ ባለቤት ወይም ግሥ የለውም ነገር ግን ሦስት ተባዕታይ ቅጽሎች።

1. መሐሪ – ቢዲቢ 337
2. ይቅር ባይ – ቢዲቢ 933
3. ጻድቅ – ቢዲቢ 843

እሱም የሚጠቅሰው ያህዌን ነው (ኤቢ፣ ገጽ 128)። ኒዶቲ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 204፣ የሚለው "መሐሪ" አስራ ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እናም ዘወትር የሚያመለክተው ያህዌን ነው፣ ከመዝ. 112፡4 በቀር። ይህም የሚያመለክተው መዝ. 112፡4 ያህዌን እንደማይጠቅስ ነው።

**112፡5** ብኪ ላይ፣ የኪዳን ወንድማማቾች ለድሀ ያለ ወለድ ያበድሩ ነበር (ዘጸ. 22:25፤ሌዋ. 25:35-38፤ዘዳ. 15:7-8)። ደሀን መርዳት ማለት አንዱ ለእግዚአብሔር ያለውን መሰጠት ማሳያ መንገድ ነው፣ እሱም ለደሀ ለሚጠነቀቀው (መዝ. 37:26፤ምሳ. 19:17፤ማቴ. 5:42፤ሉቃስ 6:35)። አንዱ ሌሎችን እንዴት እንደሚይዛቸው ያለው አገባብ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ግንኙነት በግልጽ ያመላክታል (መዝ. 112:4)

**112:6ለ** ከዚህ ስንኝና ከመዝ. 112:3ለ እና 9ለ የተነሣ፣ ከሞት በኋላ ያለው ሕይወት በተወሰነ መልኩ፣ የእግዚአብሔር መታሰቢያ ሳይሆን፣ ተመልክቷል! መንግሥተ-ሰማይ የእግዚአብሔር መታሰቢያ አይደለም ነገር ግን የእርሱ ሕዝብ ከእርሱ ጋር የሚያደርገው ኅብረት እንጂ ነው (ማቴ. 22፡31-32)።

## መዝሙር ፡112፡7-9

**7ከክፉ ነገር አይፈራም**
**በእግዚአብሔር ለመታመን ልቡ የጸና ነው።**
**8በጠላቶቹ ላይ እስኪያይ ድረስ**
**ልቡ ጽኑ ነው፥ አይፈራም።**
**9በተነ ለችግረኞችም ሰጠ**
**ጽድቁ ለዘላለም ዓለም ይኖራል**
**ቀንዱ በክብር ከፍ ከፍ ይላል።**

**112፡9ሀ** ይህ ተጠቅሷል (1 ቆሮ. 9፡9) ላይ፣ በጳውሎስ የአሕዛብ አብያተ-ክርስቲያናት ማብራሪያ ላይ፣ የአንድ ጊዜ ስጦታ በኢየሩሳሌም ላለችው እናት ቤተ-ክርስቲያን (ማለትም፣ 2 ቆሮንቶስ 8-9)።

**112፡9ሐ "ቀንዱ በክብር ከፍ ከፍ ይላል"** ይህ የብኪ ፈሊጥ ነው፣ ግለሰብ በኅብረተሰቡ ውስጥ ላለው ስፍራ። እሱም የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ሥራ ነው፣ የግለሰብን አቋም፣ ሀብት፣ እና ሥልጣን ከፍ በማድረግ። ያህዌ ይሄንን ለንጉሥ አድርጓል፣ 1 ሳሙ. 2፡10 ላይ (ደግሞም መዝ. 89፡17፣ 24 ላይ ማስታወሻ ተመልከት) ደግሞም ለሐና 1 ሳሙ. 2፡1 ላይ።

## መዝሙር ፡112፡10

**10ኃጢአተኛም አይቶ ይቈጣል፥**
**ጥርሱንም ያፏጫል፥ ይቀልጣልም**
**የኃጢአተኞችም ምኞት ትጠፋለች።**

**112:10 "ጥርሱንም ያፏጫል"** ይህ የቁጣ ምልክት ነው (መዝ. 35:16፤37:12፤112:10፤ሉቃስ 13:28)። እሱም ደግሞ ፍርድን መቀበልንም ያሳያል (ማቴ. 8:12፤13:42፣50፤22:13፤24:51፤25:30)።

▣ **"ይቀልጣል"** ኃጢአተኞች ይጠፋሉ (መዝ. 68፡2)። እነርሱም በያህዌ የፍርድ እሳት ቀልጠው ይጠፋሉ (ኢሳ. 34፡2-4)።
የእነርሱ ሥነ-ልቦናዊ ሥቃይ የተፈጠረው

1. የብልጽግና አቋማቸው በመገልበጡ
2. ከእግዚአብሔር መንግሥት በመነጠላቸው
3. ታማኝ ተከታዮች በዓይናቸው ፊት መባረካቸውና መበልጸጋቸው

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልስህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. እግዚአብሔርን "መፍራት" ምን ማለት ነው?
2. መዝ. 112፡4ሀን በገዛ ራስህ ቃላት አብራራ።
3. መዝ. 112፡3፤6፣ እና 9 ስለ መንግሥተ-ሰማይ ነው የሚናገሩትን?
4. "ቀንዱ ከፍ ከፍ ይላል" ምን ማለት ነው? (መዝ. 112፡9)

# መዝሙር 113
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር ትሑቱን ከፍ ያደርጋል<br><br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | የእግዚአብሔር ግርማ እና የተዋረዱትን መመልከት | እግዚአብሔር ትሑቱን ስለሚረዳ ማክበሪያ ውዳሴ | የእግዚአብሔርን መልካምነት ማወደስ | ለክብርና ለምሕረት አምላክ |
| 113:1-4 | 113:1ሀ | 113:1 | 113:1ሀ | 113:1ሀ |
| | 113:1ለ-3 | | 113:1ለ-4 | 113:1ለ-3 |
| | | 113:2-4 | | 113:4-6 |
| | 113:4-6 | | | |
| 113:5-9 | | 113:5-9 | 113:5-9ለ | |
| | 113:7-9ለ | | | 113:7-9ለ |
| | 113:9ሐ | | 113:9ሐ | 113:9ሐ |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡113፡1-4**

**[1]ሃሌ ሉያ።**
**የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆይ፥ አመስግኑት፥**
**የእግዚአብሔርንም ስም አመስግኑ።**
**[2]ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም ድረስ**
**የእግዚአብሔር ስም ቡሩክ ይሁን።**
**[3]ከፀሐይ መውጫ ጀምሮ እስከ መግቢያው ድረስ**
**የእግዚአብሔር ስም ይመስገን።**
**[4]እግዚአብሔር በአሕዛብ ሁሉ ላይ ከፍተኛ ነው፥**
**ክብሩም ከሰማያት በላይ ነው።**

**113፡1** ይህ ቁጥር ተመሳሳይ ተተኳሪዎች አሉት፣ ለአጽንዖት ሦስት ጊዜ የተደገሙ (ቢ.ዲ.ቢ. 237፣ ኬቢ. 248፣ ፖል ተተኳሪ፤ተመሳሳይ ብልሃትን መዝ. 96:1-2 ላይ ተመልከት)። እሱም እንደ መዝሙር 111፤ 112 ዓይነት ይጀምራል (መዝ. 111፡1 ላይ ማስታወሻ ተመልከት)። ይህ መዝሙር ያህዌ ለምን መመስገን እንዳለበት ይገልጻል።

1. ከአሕዛብ ሁሉ በላይ ስለሆነ፣ መዝ. 113፡4
2. ክብሩ ከሰማያት በላይ ስለሆነ፣ መዝ. 113፡4
3. እሱ ልዩ ስለሆነ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት)፣ መዝ. 113፡5
4. እሱ ራሱን ትሑት ያደርጋል፣ ለማወቅና በእሱ ታማኝ ተከታዮች ሕይወት ውስጥ ለመግባት፣ መዝ. 113:6 (መዝ. 18:35ሐ)
5. ከማኅበረሰቡ ለተገለሉትና ኃይል ለሌላቸው ክብካቤ ያደርጋል መዝ. 113:7-9 (መዝ. 109:31)

*ሀ. ደሀ*

ለ. ችግረኛ
ሐ. መጠጊያ የሌላቸው

▣ **"እግዚአብሔር"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ **"የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆይ"** ኤቢ (ገጽ 131) አናባቢዎቹን ለውጦ "የእግዚአብሔር *ሥራዎች*" የሚል ያደርገዋል። ይህ መልክ (ቢዲቢ 714) መክ. 9፡1 ላይ ይገኛል።

ኤምቲ ልክ ከሆነ፣ "ባሪያዎች" የሚያመለክተው

1. መላእክትን (መዝ. 103:20-22)
2. በመቅደስ ያሉ ምዕመናንን (አምላኪዎችን) (ዘዳ. 32:43፤መዝ. 34:22፤69:36፤105:25፤135:14)
3. ሌዋውያን/ካህናት በመቅደስ (መዝ. 134:1፤135:1-2)

▣ **"የእግዚአብሔር ስም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" ያየህዌ።

**113፡2 "ይባረክ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ *ፖል* አንቀጽ ተጽዕኗዊ መልክ ካለው ግሥ ጋር ተደባልቋል "የመሆን ግሥ") "ከማመስገን" ጋር ትይዩ ነው" (መዝ. 145:21)።

**113:2ለ-3ሀ** እነዚህ ሁለት ስንኞች (መስመሮች) ትይዩና በዘይቤአዊ ቋንቋ ናቸው፣ የያህዌን የምስጋና ዳርቻ ለመግለጽ

1. ለሁል ጊዜ፣ መዝ. 113:2ለ
2. በሁሉም ስፍራ፣ መዝ. 113:3ሀ

**113:4 "በአሕዛብ ሁሉ ላይ"** ይህ ቁጥር እሱ ለምን እንደሚመሰገን ይገልጻል።

1. እሱ ከአሕዛብ ሁሉ በላይ ነው (መዝ. 97:9፤99:2)
2. ክብሩም ከሰማያት በላይ ነው (መዝ. 8:1፤57:11፤148:13)

▣ **"ክብር"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ክብር።

***መዝሙር ፡113፡5-9ሐ***

**5 እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ማን ነው?**
**በላይ የሚኖር**
**6 በሰማይና በምድር**
**የተዋረዱትን የሚያይ**
**7-8 ከአለቆች ጋር**
**ከሕዝቡም አለቆች ጋር ያኖረው ዘንድ**
**ችግረኛን ከመሬት የሚያነሣ፥**
**ምስኪኑንም ከፋንድያ ከፍ ከፍ የሚያደርግ**
**9 መካኒቱን በቤት የሚያኖራት፥**
**ደስ የተሰኘችም የልጆች እናት የሚያደርጋት።**
**ሃሌ ሉያ።**

**113፡5 "እንደ አምላካችን እንደ እግዚአብሔር ማን ነው?"** ሁለቱም ያህዌ እና ኤሎሂም ለእስራኤል አምላክ ጥቅም ላይ እንደዋሉ ተገንዘብ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች)።

▣ **"በላይ የሚኖር"** ይህ ከመዝ. 113፡4ለ ጋር ትይዩ ነው። እሱም ለንግሥና ፈሊጥ ነው (መዝ. 103፡19)። ያህዌ ንጉሥ ነው (1 ሳሙ. 8፡7 ተመልከት)። የጥንቶቹ እስራኤላውያን አምላካቸውን ይመለከቱት የነበረው በዙፋኑ ላይ ተቀምጦ ነው፣ በምድር ከባቢ አየር ላይ እግሩን አኑሮ (ማለትም፣ የእግሩ መቀመጫ) በኪዳኑ ታቦት ላይ። የታቦቱ መክደኛ ምድርና ሰማይ የተገናኙበት ነበር፣ ከተምሳሊት አኳያ!

**113:6**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀቅ** | **"ራሱ ትሑት የሆነ"** |
| **አየተመቅ** | **"የተዋረዱትን የሚያይ"** |
| **አእቅ፣ አእት** | **"ወደ ታች የሚመለከት"** |
| **አኢመቅ** | **"ወደ ታች ለመመልከት የሚቆም"** |
| **ጄፒኤስአኤ** | **"ከታች ያለውን የሚመለከት"** |
| **የተእመቅ** | **"ወደ ታች የሚመለከት"** |

ይህ ያልተለመደ ሐረግ የሚገልጸው ያህዌ በምድር ላይ ምን እየሆነ እንዳለ እንደሚያውቅ ነው፣ በተለይም በሕዝቡ ላይ (ዘጸ. 3:7-8፤መዝ. 138:6ሀ፣ለ)።

LXX ቁጥሩን የሚተረጉመው ያህዌ "የተዋረዱትን" እንደሚመለከት ነው (ማለትም፣ ሰዎችን)።

ፔሺታ የሚተረጉመው "ጥልቅ" በሚል ነው፣ እናም ከዚህ ዓለም ሦስት ዕርከኖች አንዱ ያደርገዋል።

1. ከባቢ አየር

2. ምድር
3. ውኃ

▣ **"በሰማይና በምድር"** ይህ ስለዚህ ዓለምና ስለ ከባቢ አየሩ የሚናገር ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማይ

**113፡9ሀ፣ለ** ሁሉም የጥንት አባቶች ሚስቶች መካኖች ነበሩ፣ ነገር ግን ያህዌ ማኅፀናቸውን ከፈተ።

1. ሳራ – ዘፍ. 21:6
2. ርብቃ – ዘፍ. 25:21
3. ራሔል – ዘፍ. 30:22-23

ሆኖም፣ ሕፃን የእግዚአብሔር ልዩ ድርጊት ነው፣ የሚያሳየውም

1. የእርሱን ክብካቤ
2. የእርሱን ኃይል
3. እርሱ ለእስራኤል እና ለሞላው ዓለም ያለውን ዕቅድ (መዝ. 113፡4)

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

**113፡9ሐ** መዝሙሩ የሚጨርሰው እንዳጀማመሩ ነው። አንዳንድ ሊቃውንት ይህንን ስንኝ (መስመር) የሚመለከቱት እንደ ቀጣዩ መዝሙር መጀመሪያ አድርገው ነው (LXX)። ይህ ሐረግ የመዝሙር 111፤ 112፤ 113 መግቢያ ነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የእግዚአብሔርን መግለጫዎች ዘርዝር።
2. እግዚአብሔር ራሱን እንዴት ትሑት ያደርጋል?
3. የትኛው ሐረግ ነው ስለ አሀዳዊነት (በአንድ አምላክ ማመን) የሚናገረው?

# መዝሙር 114
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር እስራኤልን ማዳን ከግብፅ<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | የእግዚአብሔር ኃይል እስራኤልን በማዳኑ | እግዚአብሔርን ለማመስገን ውዳሴ፣ ስለ ታላቅ ሥራው፣ ሕዝቡን በማቋቋሙ | የደስታ ስሜት መዝሙር | የፋሲካ መዝሙር |
| 114:1-2 | 114:1-2 | 114:1-2 | 114:1-2 | 114:1ሀ |
| | | | | 114:1ለ-2 |
| 114:3-6 | 114:3-6 | 114:3-4 | 114:3-4 | 114:3-4 |
| | | 114:5-6 | 114:5-6 | 114:5-6 |
| 114:7-8 | 114:7-8 | 114:7-8 | 114:7-8 | 114:7-8 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ሦስተኛው አንቀጽ*
4. *ወዘተርፈ*

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡114፡1-2**
**[1]እስራኤል ከግብጽ፥**
**የያዕቆብም ቤት ከእንግዳ ሕዝብ በወጣ ጊዜ፥**
**[2]ይሁዳ መቅደሱ፥**
**እስራኤልም ግዛቱ ሆነ።**

**114፡1-2** ይህ መዝሙር ስለ ዘጸአት ነው ከግብፅ (ዘጸአት 1-12)። ዘጸአት ቀጥተኛ ፍጻሜ ነው፣ ያህዌ ለአብርሃም ያደረገው መገለጥና ተስፋ፣ ዘፍ. 15፡12-21 ላይ። ዘጸአት የእግዚአብሔር ሕዝብ መጀመሪያ ነው (ዘጸአት 19-20)።
የእግዚአብሔርን ሕዝብ የተለያዩ መጠሪያዎች አስተውል።
1. እስራኤል
2. የእስራኤል ቤት
3. ይሁዳ

**114፡1 "እስራኤል"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እስራኤል (ስሙ)።

▣ **"ከእንግዳ ሕዝብ"** ይህ ሐረግ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ። ኤቢ (ገጽ 134) ተመሳሳይ ተናባቢዎችን ወስዶ ዳግመኛ ያናብባቸዋል፣ ከኢሳ. 25፡3 ጋር ለማስማማት፣ እዚያም "ጨካኝ ሰዎች" በሚል የሚገልጸው (ቢዲቢ 470፣ ማለትም፣ የእስራኤላውያን አስገባሪዎች፣ ዘጸ. 3:7)። ተመሳሳይ ሥር ጥቅም ላይ ውሏል፣ በላሜድ አጽንዖታዊ ፊደል (ማለትም፣ የዕብራይስጥ ፊደል ኤል) ሰቆ. 4፡3 ላይ።

እስራኤል ከባዕድ ገዥዎች ሥር የሚሆንበት ታሪካዊ እውነታ ተደጋጋሚ ነው (ኢሳ. 28:22፤33:19፤ኤር. 5:15)። የትርጓሜ ጥያቄ የሚሆነው የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዴት በጣዖት አምላኪዎች ገዥነት ሥር መሆኑ ነው (ዕንባቆም)። እግዚአብሔር የከነአንን ነገዶች

በኃጢአታቸው ምክንያት ከምድሩ ላይ እንዳስወጣ፣ እንዲሁ ደግሞ እስራኤላውያንን በኃጢአታቸው ምክንያት (ማለትም፣ የአሦር፣ ባቢሎን፣ እና የፋርስ ግዞት)።

**114፡2** ሁለቱም ይሁዳና እስራኤል በመጠቀሳቸው ምክንያት፣ አንዱ ሊደነቅ ይችላል ይህ መዝሙር መቼ እንደተጻፈ።

1. የተባበረው መንግሥት ሲያበቃ ከሳኦል — ሰሎሞን
2. በ922 ቅ.ል.ክ. መንግሥቱ ተከፈለ
   ሀ. ሮቦሀም በይሁዳ
   ለ. ጀሮቦአም I በእስራኤል
3. ከፋርስ ግዞት መመለስ በኋላ፣ በቂሮስ II ሥር፣ እስራኤላውያን በድጋሚ የአብሮነት ስማቸውን ወሰዱ፣ ምንም እንኳ የይሁዳን ነገድ ስፍራ አነስተኛ ክፍል ብቻ ቢይዙም (ማለትም፣ በኢየሩሳሌም ዙሪያ አነስተኛ ስፍራ)

▣ ***"መቅደሱ"*** ይህ የሚያመለክተው

1. በኢየሩሳሌም በሞሪያ ተራራ ያለውን መቅደስ
2. የከነአንን ሙሉውን ምድር እንደ ያህዌ ልዩ ርስት

▣ ***"ግዛቱ"*** ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 606) ሁለት ፍችዎች አሉት።

1. የያህዌ ዩኒቨርሳላዊ ግዛት/አገር፣ መዝ. 103:22፤145:13 (ኢያሱ 3፤11፤13)
2. ከነአን እንደ ያህዌ የተለየ ርስት (ማለትም፣ የተስፋይቱ ምድር፣ ዘጸ. 15:17)

***መዝሙር ፡114፡3-6***

**[3]ባሕር አየች ሸሸችም፥**
**ዮርዳኖስም ወደ ኋላው ተመለሰ።**
**[4]ተራሮች እንደ ኮርማዎች፥**
**ኮረብቶችም እንደ ጠቦቶች ዘለሉ።**
**[5]አንቺ ባሕር የሸሸሽ፥**
**አንቺም ዮርዳኖስ ወደ ኋላሽ የተመለስሽ፥ምን ሆናችኋል?**
**[6]እናንተም ተራሮች፥ እንደ ኮርማዎች፥**
**ኮረብቶችስ፥ እንደ ጠቦቶች ለምን ዘለላችሁ?**

**114፡3-6** ይህ ዘይቤአዊ ቋንቋ ነው (መዝ. 18:7-15፤29:3-9፤68:7-8፤77:16-19)። በዚህ አካባቢ የብኪ ግነታዊ ዘይቤ እና ምናባዊ ምስያ ለግንዛቤ እጅግ የረዱኝ ሁለቱ መጻሕፍት

1. ዲ. ብሬንት ሳንዲ፣ የማረሻ አፍሬ (ስለት) እና ቆልማማ መቁረጫ ፡ የመጽሐፍ ቅዱስን ትንቢታዊና የፍጻሜ ዘመን ጽሑፍን ቋንቋ ዳግም ማሰላሰል (መመርመር)
2. ጂ. ቢ. ኬርድ፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ እና ምናባዊነት

"ውኃ" በበርካታ መልኩ መጠቀሱ ጠቃሚ ነው። ውኃ ብቸኛው ነገር ነው፣ ዘፍጥረት 1 ላይ መፈጠሩ ተለይቶ ያልተጠቀሰ። ውኃ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) አፈ-ታሪክ መለኮት ነበር (ማለትም፣ ጨውማ ውኃ፣ ንጹሕ ውኃ)። በውኃና በአማልክት መካከል ግጭት ነበር። መጽሐፍ ቅዱስ ይሄንን ምናባዊ ምስያ አዘውትሮ የሚጠቀመው ያህዌን ለመግለጽ ነው (ኢዮብ 41:1፤መዝ. 74:12-17፤ኢሳ. 27:1)። ያህዌ ሌዋታንን ተቆጣጥሮታል ኢዮብ 3:8 ላይ፤መዝ. 104:26። ግን ደግሞ "ባሕር" ሰውኛ ዘይቤ መሆኑን ተገንዘብ መዝ. 114:3፤5 ላይ (ከሌሎቹ የተፈጥሮ ገጽታዎች ጋር)።

ሆኖም፣ መዝ. 114:8 ላይ ሕይወት ሰጪው የውኃ ገጽታ ነው የተቀመጠው። ያህዌ ነው የበረከት ምንጭ፣ በአል ሳይሆን (ማለትም፣ ዝናብ)።

ውኃን እና የብስን (ደረቁን መሬት) የመለያየቱ ምናባዊ ምስያ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) የሚወሰደው ለመነሻ ፍጥረት ጠቃሽ ነው። የሥጋዊ ፍጥረት ግብ የእግዚአብሔር ሕዝብ ፍጥረት ነው። የፍጥረት ዓላማ ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት ማድረግ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

**114፡3 "ባሕር አየች ሸሸችም፥"** ይህ የሚያመለክተው

1. "የኤርትራን ባሕር" ማቋረጥ ("የባሕር ደንገል፣" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የኤርትራ ባሕር)፣ እሱም ዘጸአት 14 እና የሙሴ ቅኔ ዘጸአት 15 ላይ የተገለጸ፤ እግዚአብሔር አደረገው
   ሀ. የሙሴን በትር በመጠቀም
   ለ. በብርቱ የምስራቅ ነፋስ
2. የዮርዳኖስን ወንዝ ማቋረጥ፣ ጎርፉ እንደ ሞላ (ኢያሱ 3)፤ ሙሉውን የትርጓሜ ማስታወሻ ተመልከት ኢያሱ 3 ላይ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር፤ እግዚአብሔር በላይኛው የወንዙ ተፋሰስ በመሬት መንሸራተት አደረገው፣ እሱም በተገቢው ሰዓት የጀመረና በተገቢው ሰዓት የተጠናቀቀ

**114፡4፤6** የከነአን ዐቢይ የፍጥረት ምድብ በያህዌና በእርሱ ሕዝብ መምጣት ይደሰታል (መዝ. 96፡9)። ይህም "መንቀጥቀጥ" በሚለው ቃል ተተኳሪ ይገለጻል፣ (ቢ.ዲ.ቢ. 296፣ ኬቢ. 297)፣ እሱም ሁለቱንም ይገልጻል

1. በፍርሃት መንቀጥቀጥ (1 ዜና. 16:30)
2. በደስታ መዝለል (መዝ. 87:7፤96:9)

**114:4 "ተራሮች"** ይህ የሚያመለክተው ሲና ተራራን ነው፣ ነገር ግን ምናልባት የከነአንን "ተራሮች" (ማለትም፣ ኮረብቶች)።

**114:6** ቁጥሩ የመዝ. 114:4ን ግሥ እንደሚደግም ተመልከት።

1. መዝለል፣ መዝ. 114:4 – *ቃል* የተጠናቀቀ
2. መዝለል፣ መዝ. 114:6 – *ቃል* ያልተጠናቀቀ

መዝሙር 114:5-6 ተፈጥሮ "ለምን" በብርቱ እንዳደረገ ጥያቄውን ያቀርባል። ምክንያቱም በፈጣሪ መገኘት ነው። በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ የሚሆነው ትዕይንት ይቀጥላል!

**መዝሙር :114:7-8**

**7ከያዕቆብ አምላክ ፊት፥**
**ከጌታ ፊት ምድር ተናወጠች**
**8ድንጋዩን ወደ ውኃ መቆሚያ፥**
**ጭንጫውንም ወደ ውኃ ምንጭ ከለወጠ።**

**114:7** ምድር በአካላዊነት ትናወጣለች፣ በፈጣሪዋ መገኘት።

እሱ እዚህጋ "ጌታ" (አዶን) ተብሎ መጠራቱን ተገንዘብ "ጌታ" (ያህዌ) ሳይሆን፣ መዝ. 114:7ሀ እና ኤሎሀ 114:7ለ ላይ እንደሆነው ሁሉ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

**114:8** ቁጥሩ ሁለት የተለዩ ሁኔታዎችን ይጠቅሳል፣ በምድረ-በዳ የመዞር ጊዜ፣ እዚያም ያህዌ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ መልኩ ሕይወት-ሰጭውን ውኃ የሰጣቸው (መዝ. 78:15፤105:41)።

1. ዘጸአት 17:6
2. ዘኍልቍ 20:11

እሱም የፍጻሜ ዘመኑን ጊዜ ለመግለጽ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ኢሳ. 48:21 ላይ (ማለትም፣ ሁለተኛው ዘጸአት)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የትኛውን የእስራኤል የታሪክ ጊዜ ነው ይህ መዝሙር የሚጠቅሰው?
2. የተፈጥሮ ሰውኛ ዘይቤ መሆን ሥነ-መለኮታዊ ዓላማው ምንድነው?
3. እግዚአብሔር ውኃን መቆጣጠሩ እጅግ ጠቃሚ የሆነው ለምንድነው?
4. "መንቀጥቀጥ" የሚለው ቃል ድርብ ፍች ይኼንን መዝሙር ለመገንዘብ እንዴት ይረዳል?

# መዝሙር 115
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የባዕድ ጣዖታት ከጌታ ጋር በተቃርኖ<br><br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | የጣዖታት ከንቱነትና የእግዚአብሔር ታማኝነት | የጌታን ኃይልና የባዕድ አማልክትን ደካማነት የሚያቃርን ትምህርት | አንዱ ብቸኛው አምላክ | አንዱ ብቸኛው አምላክ |
| 115:1-8 | 115:1-2 | 115:1-2 | 115:1 | 115:1-2 |
| | | | 115:2-8 | |
| | 115:3-8 | 115:3-8 | | 115:3-4 |
| | | | | 115:5-6 |
| | | | | 115:7-8 |
| 115:9-15 | 115:9-11 | 115:9-11 | 115:9-11 | 115:9-11 |
| | 115:12-13 | 115:12-13 | 115:12-13 | 115:12-13 |
| | 115:14-15 | 115:14-15 | 115:14-15 | 115:14-15 |
| 115:16-18 | 115:16-18ለ | 115:16-18 | 115:16-18ለ | 115:16 |
| | | | | 115:17-18ለ |
| | 115:18ሐ | | 115:18ሐ | 115:18ሐ |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር በሰው ሥራሽ ጣዖታት የመታመንን ከንቱነት የሚገልጽ ነው። አንዱ እውነተኛ ፈጣሪ/ተቤዢ መለኮት ብቻ ነው ሊታመን የሚገባው።

ለ. ይህ መዝሙር የተደጋጋሚ ሐረጋት ባሕርይ አለው።
1. “ለእኛ አይደለም፣” ሁለቴ ተደግሟል፣ መዝ. 115፡1
2. “እነርሱ...” ሰባት ያልተጠናቀቁ፣ መዝ. 115፡5-7
3. “መታመን፣” አራት (ሦስት ተተኳሪዎች እና አንድ አንቀጽ፤ የጥንቶቹ ቅጅዎች እንደ LXX፣ ፔሺታ፣ እና ቫልጌት ያሉት፣ የኤምቲን ተተኳሪዎች የሚተረጒሙት እንደ ተጠናቀቁ ነው)፣ መዝ. 115፡8-11
4. “ይባርካል...” ስድስት (ስድስት ፔል ተተኳሪዎች እና አንድ ቃል ተገብሮ አንቀጽ)፣ መዝ. 115:12- 15፤18
5. “ሃሌ ሉያ”
   ሀ. በአሉታዊ፣ 115:17 (ፒል ያልተጠናቀቀ)
   ለ. ትእዛዛዊ፣ መዝ. 115:18 (ፒል ተተኳሪ)

ሐ. LXX እና አንዳንድ የዕብራይስጥ ኤምኤስኤስ መዝሙር 114 እና 115ን ይደባልቃሉ።

**መዝሙር ፥115፥1-8**

**[1]ለእኛ አይደለም፥ አቤቱ፥ ለእኛ አይደለም፥**
**ነገር ግን ለስምህ**
**ስለ ምሕረትህ ስለ እውነትህም ምስጋናን ስጥ።**
**[2]አሕዛብ።**
**አምላካቸው ወዴት ነው? አይበሉ።**
**[3]አምላካችንስ በላይ በሰማይ ነው**
**በሰማይም በምድርም የፈቀደውን ሁሉ አደረገ።**
**[4]የአሕዛብ ጣዖታቶች የወርቅና የብር፥**
**የሰው እጅ ሥራ ናቸው።**
**[5]አፍ አላቸው አይናገሩምም**
**ዓይን አላቸው አያዩምም**
**[6]ጆሮ አላቸው አይሰሙምም**
**አፍንጫ አላቸው አያሸትቱምም**
**[7]እጅ አላቸው አይዳሰሱምም**
**እግር አላቸው አይሄዱምም**
**በጉሮሮአቸውም አይናገሩም።**
**[8]የሚሠሩአቸውም የሚያምኑባቸውም ሁሉ**
**እንደ እነርሱ ይሁኑ።**

**115፥1-8** ይህ አንጓ ስለ ጣዖታት ከንቱነት ነው! አንድ አምላክ ብቻ ነው ያለው (ኤር. 10:6-10፤ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት (በአንድ አምላክ ማመን))! "ለአሕዛብ" አንድ ተስፋ ብቻ ነው ያለው። ሁሉም የመጽሐፍ ቅዱስ ተማሪዎች ቅድመ-ግምት አላቸው፣ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ "ዋነኛ ትረካ" (ማለትም፣ ስለ እሱ መሠረታዊ ዓላማ ወይም መልእክት)። ያህዌ አሕዛብ እንዲታመኑበት ያለው ሐሳብ የእኔ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

**115፥1** እንዴት ያለው ብርቱ ቁጥር ነው። ክብር (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ክብር) ለያህዌ ብቻ ነው የሚገባው፣ ለማንም የሰው ወኪል ወይም ወገን ሳይሆን። ይሄም የሆነበት ምክንያት

1. በያህዌ ምሕረት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት [ሄስድ])
2. በያህዌ ታማኝነት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ፤ ደግሞም ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት)
3. ያህዌ ሉዓላዊ ነው፣ መዝ. 115:3 (መዝ. 103:19፤135:5-6)
4. ያህዌ ይሰማል ያደርጋልም፣ ጣዖታት ግን አይችሉም፣ መዝ. 115:4-7 (መዝ. 135:15-18፤ዘዳ. 4:28፤ኢሳ. 44:12-17፤ኤር. 10:3-5)
5. ያህዌ ፈጣሪ ነው፣ "ሰማይና ምድርን የሠራ" (መዝ. 115:15ለ፣16)

▣ **"ስምህ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ።

**115፥2** የስንኙ (መስመር) 2 ጥያቄ የሥነ-መለኮት ጉዳይ ነው። እስራኤል እንድትሆን የታሰበው የካህናት መንግሥት ነበር (ዘጸ. 19፥5-6) ዓለምን ለመርዳት፣ ያህዌን እንዲያውቅና እንዲገነዘብ። ነገር ግን በእርሷ አለማመን ምክንያት ዓለም ያየው የእግዚአብሔርን ፍርድ ብቻ ነው (ሕዝ. 36፡ 22-38)።

የመስመር 2 ዋነኛ ጥያቄ መዝ. 42:3፤79:10 (ኢዩኤል 2:17፤ሚክያስ 7:10 ላይ ተደግሟል)።

**115፥4 "ብርና ወርቅ"** እነዚህ የከበሩ ድንጋዮች ናቸው፣ በድንጋይ ወይም በእንጨት ቅርጾች ላይ የሚፈስሱ (የሚለበጡ)።

**115፥7ለ** መዝ. 115፥5 "ንግግር፣"ን በመጥቀሱ ምክንያት፣ ይህ አንድ ዓይነት መናፍስት ጠሪነትን የሚያመለክት ይሆናል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መናፍስት ጠሪ) በባዕድ አምልኮ ጣዖታት ስም የሚደረግ። ዘዳ. 18፥10-11 ያለውን ማስታወሻ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ተመልከት።

**115፥8** ይህ ቁጥር እውቅና ይሰጣል፣ ሰዎች እንደሚያመልኩት አማልክት ዓይነት ይሆናሉ ለሚለው እውነት። እፎይ፣ አማኞች እጅጉን እንደ ኢየሱስ ይመስላሉ! የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ግብ አንድ ቀን በመንግሥተ-ሰማይ የሚሆን ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን አሁን ክርስቶስን መምሰል እንጂ (ሮሜ. 8:28-29፤2 ቆሮ. 3:18፤7:1፤ ገላ. 4:19፤ ኤፌ. 1:4፤ 4:13፤ 1 ተሰ. 3:13፤ 4:3፣7፤ 5:23፤ 1 ጴጥ. 1:15)። ሕይወትህ የምታመልከውን ያንጸባርቃልን?

**መዝሙር ፥115፥9-15**

**[9]የእስራኤል ቤት ሆይ፥ በእግዚአብሔር ታመኑ**
**ረድኤታቸውና መታመኛቸው እርሱ ነው።**
**[10]የአሮን ቤት ሆይ፥ በእግዚአብሔር ታመኑ**
**ረድኤታቸውና መታመኛቸው እርሱ ነው።**

[11]**እግዚአብሔርን የምትፈሩ ሆይ፥ በእግዚአብሔር ታመኑ**
**ረድኤታቸውና መታመኛቸው እርሱ ነው።**
[12]**እግዚአብሔር አሰበን ይባርከንማል**
**የእስራኤልን ቤት ይባረካል፥**
**የአሮንንም ቤት ይባረካል።**
[13]**እግዚአብሔርን የሚፈሩትን፥**
**ትንንሾችንና ትልልቆችን ይባርካል።**
[14]**እግዚአብሔር በላያችሁ፥**
**በላያችሁና በልጆቻችሁ ላይ ይጨምር።**
[15]**እናንተ ሰማይንና ምድርን ለሠራ**
**ለእግዚአብሔር የተባረካችሁ ናችሁ።**

**115፡9-15** ሦስትዮሹን መጠሪያ እና ትዕዛዝ ተገንዘብ (*"መታመን፣"* ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል ተተኳሪ*)።
1. እስራኤል ሆይ፣ በእግዚአብሔር *ታመኑ*፣ መዝ. 115:9፣12
2. የአሮን ቤት ሆይ፣ በእግዚአብሔር *ታመኑ*፣ መዝ. 115:10፣12
3. እግዚአብሔርን የምትፈሩ/የምታከብሩ እናንተ፣ *ታመኑት*፣ መዝ. 115:11፣12 (ይህም ተጨማሪ ባሕርይ ሊሆን ይችላል፣ የቁ. 1 እና 2፣ መዝ. 135:19-20፣ ወይም እስራኤላዊ ያልሆኑትን መጥቀሻ 1 ነገ. 8:41-43፤ ዕዝራ 6:21፤ ነሀ. 10:28)

በምላሹም ያህዌ ይሆናል
1. *ረዳታቸው* (መዝ. 18:2፤33:20፤70:5፤121:2፤124:8፤146:5)
2. *ጋሻቸው* (መዝ. 28:7፤59:11፤84:9፣11፤119:114፤144:2)
3. *ያስብልናል* (መዝ. 98:3)
4. *ሁለቱንም ታላላቆችንም ታናናሾችንም ይባርካል*
5. *በላያችሁና በልጆቻችሁ ላይ ይጨምራል* (ቢዲቢ 414፣ ኬቢ 418፣ *"መጨመር" ሂፊል ተጽዕኗዊ*፣ መዝ. 112:2)

ጣዖትን በማምለክ ላይ በጊዜና በዘላለማዊነት መዘዝ አለው! በያህዌ ላይ ባለ የግል እምነትና ታማኝነት ውጤት አለው (መዝ. 115:16-18)!

***መዝሙር* :115፡16-18**

[16]**የሰማያት ሰማይ ለእግዚአብሔር ነው**
**ምድርን ግን ለሰው ልጆች ሰጣት።**
[17]**አቤቱ፥ ሙታን የሚያመሰግኑህ አይደሉም**
**ወደ ሲኦልም የሚወርዱ ሁሉ**
[18]**እኛ ሕያዋን ግን ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም**
**እግዚአብሔርን እንባርካለን፦**
**ሃሌ ሉያ።**

**115፡16ሀ *"የሰማያት ሰማይ ለእግዚአብሔር ነው"*** ይህ የእግዚአብሔርን ዙፋን ያመለክታል (ማለትም፣ እጅግ ከፍተኛውን ሰማይ)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማያት እና ሦስተኛው ሰማይ።

**115፡16ለ** እግዚአብሔር ምድርን ለሰው ልጆች ማደሪያና ቁጥጥር ሥር እንድትሆን አድርጓታል (መዝ. 8፡6)። ሆኖም፣ እርሷ የእሱ ነች (ዘዳ. 10፡14) እርሱ ስለ ሠራት (መዝ. 121:2፤124:8፤134:3)።

**115:17 *"ሙታን"*** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው?

**115:18** የእግዚአብሔር ሕዝቦች ዘላለም ይባርኩታል (*ፒል ያልተጠናቀቀ*) ያመሰግኑታልም (*ፒል ተተኳሪ*) ያህዌን። ይህም በአንድምታው ከዚህ ሕይወት በኋላ ከጣዖት አምላኪዎች ጋር የሚኖረውን መለያየት ነው "ከማያመሰግኑት" እናም "ወደ ጸጥታ ይወርዳሉ" (መዝ. 6:5፤30:9፤88:10-11፤ 94:17)።

▣ ***"ሃሌ ሉያ"*** እንደ መዝ. 113:9ሐ፣ LXX ይሄንን ወደ ቀጣዩ መዝሙር መጀመሪያ ያዘረዋል።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የብኪዎቹን ቃላት አብራራ
   ሀ. ምሕረት
   ለ. ታማኝነት/እውነት
2. ሁለቱም መዝ. 115፡1 እና 2ከሥነ-መለኮት አኳያ እጅግ ጠቃሚ የሚሆኑት ለምንድነው?
3. ያህዌ ከአምልኮተ-ባዕድ ጣዖታት እንዴት ይለያል?
4. መዝ. 115፡9-11 የሚያመለክተው አንድ ወገንን (ቡድን)፣ ሁለት ወገንን፣ ወይስ ሦስት ወገንን ነውን?
5. ያህዌ ለታማኝ ተከታዮች የሚያደርጋቸውን ነገሮች ዘርዝር።
6. መዝ. 115፡16ን በገዛ ራስህ ቃላት አብራራ።
7. “ወደ ጸጥታ ስፍራ (ሲኦል) የሚወርዱ” የሚለውን፣ መዝ. 115፡17ለ ላይ ያለውን አብራራ

# መዝሙር 116
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ምስጋና ከሞት በመታደጉ<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | ምስጋና ከሞት በመታደጉ | ምስጋና ስለ ፈውስ | አንዱ ከሞት የዳነ ጌታን ሲያመሰግን | ምስጋና ማቅረብ |
| 116:1-4 | 116:1-2 | 116:1-4 | 116:1-4 | 116:1-2 |
| | 116:3-4 | | | 116:3-4ሀ |
| | | | | 116:4ለ |
| 116:5-11 | 116:5-7 | 116:5-7 | 116:5-7 | 116:5-6 |
| | | | | 116:7-9 |
| | 116:8-11 | 116:8-11 | 116:8-11 | |
| | | | | 116:10-13 |
| 116:12-19 | 116:12-14 | 116:12-19 | 116:12-14 | |
| | | | | 116:14 |
| | 116:15 | | 116:15-19ለ | 116:15 |
| | 116:16-17 | | | 116:16-17 |
| | 116:18-19ለ | | | 116:18-19 |
| | 116:19ሐ | | 116:19ሐ | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡116፡1-4**
**[1]እግዚአብሔር የልመናዬን**
**ድምፅ ሰምቶአልና ወደድሁት።**
**[2]ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሎአልና**
**በዘመኔ ሁሉ እጠራዋለሁ።**
**[3]የሞት ጣር ያዘኝ፥**
**የሲኦልም ሕማም አገኘኝ**
**ጭንቀትንና መከራን አገኘሁ።**
**[4]የእግዚአብሔርንም ስም ጠራሁ።**
**አቤቱ፥ ነፍሴን አድናት።**

**116፡1-4** *ይህ መዝሙር የተጻፈው ሞትን በተጋፈጠ ታማኝ ተከታይ ነው* (መዝ. 116፡3)። እሱም የሐሳቡን ሂደት ይገልጻል፣ በዚህ ሁኔታ ውስጥ እንዴት እንደሚሆን።

1. ማረጋገጫ – ጌታን እወደዋለሁ፣ ቢዲቢ 12፣ ኬቢ 17፣ *ቃል* የተጠናቀቀ (ዘዳ. 6:5፤30:6፤መዝ. 31:23)
2. ያህዌን ለምን ይወድዳል
   ሀ. ጸሎቴን ሰምቷልና፣ ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
   ለ. ጆሮውን ወደ እኔ አዘንብሏልና (ከሀ ጋር ትይዩ)፣ ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ *ሂፊል*የተጠናቀቀ
3. ውጤት – እጠራዋለሁ፣ ቢዲቢ 894፣ ኬቢ 1128፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
4. የመዝሙረኛው ሁኔታ
   ሀ. የሞት ጣር (መዝ. 18:4-5) ያዘው፣ ቢዲቢ 67፣ ኬቢ 79፣ *ቃል* የተጠናቀቀ
   ለ. ጣር (ቢዲቢ 865 ሁለቴ፣ የጭንቀት፣ መዝ. 118:5፤ሰቆ. 1:3) የሲኦል መጣብኝ ("አገኘው" ቢዲቢ 592፣ ኬቢ 619፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) እሱን (ልዩ ርዕስ ተመልከት: ሙታን የት ናቸው?)
5. መደምደሚያ – የእግዚአብሔርን ስም ጠራሁ፣ ቢዲቢ 894፣ ኬቢ 1128፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
   የእርሱ ቃላት፣ "አምላኬ ሆይ፣ እለምንሃለሁ፣ ሕይወቴን አድን፣" ቢዲቢ 572፣ ኬቢ 589፣ *ፒኤል* ተተኳሪ

**መዝሙር ፡116፡5-11**

**5 እግዚአብሔር መሓሪና ጻድቅ ነው፥**
**አምላካችንም ይቅር ባይ ነው።**
**6 እግዚአብሔር ሕፃናትን ይጠብቃል**
**ተቸገርሁ እርሱም አዳነኝ።**
**7 ነፍሴ ሆይ፥ ወደ ዕረፍትሽ ተመለሺ፥**
**እግዚአብሔር መልካም አድርጎልሻልና**
**8 ነፍሴን ከሞት፥**
**ዓይኔንም ከእንባ፥**
**እግሬንም ከመሰናከል አድኖአልና።**
**9 በሕያዋን አገር**
**በእግዚአብሔር ፊት እሄዳለሁ።**
**10 አመንሁ ስለዚህም ተናገርሁ**
**እኔም እጅግ ተቸገርሁ።**
**11 እኔም ከድንጋጤዬ የተነሣ።**
**ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው አልሁ።**

**116፡5-11** *መዝሙረኛው ከጸለየ በኋላ የያህዌን ባሕርይ በጥልቀት ይመለከታል* (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት)።

1. መሐሪ
2. ጻድቅ
3. የሚራራ
4. ሕፃናትን የሚጠብቅ (ቢዲቢ 834፣ ኬቢ 989፣ ያልሠለጠነ ወይም የዋህ ሰው፣ ነገር ግን ለትእዛዝ ክፍት የሆነ፣ መዝ. 19:7)

ያህዌ ባሕርዩን አሳይቷል።

1. እሱ አዳነኝ – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 440፣ *ሂፊል*ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 116:6ለ
2. ወደ ዕረፍት መለሰኝ – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ *ቃል* ተተኳሪ (እሱ ለራሱ ነው የሚናገረው፣ በአእምሮው የደኅንነትና የጥበቃ ስፍራ፣ በያህዌ)፣ መዝ. 116:7ለ
3. እሱ ለእርሱ በተትረፈረፈ መልኩ አድርጎለታል (መዝ. 13:6፤119:17፤142:7)፣ መዝ. 116:7ለ
4. ነፍሴን አድኗታል (ማለትም፣ ኔፊሽ፣ ቢዲቢ 659) ከሞት – ቢዲቢ 322፣ ኬቢ 321፣ *ፒኤል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 116:8ሀ
5. ዓይኖቼን ከዕንባ ጠብቋል፣ መዝ. 116:8ለ
6. እግሮቼን ከመሰናከል ጠብቋል፣ መዝ. 116:8ሐ (መዝ. 56:13)

የመዝሙረኛው ምላሽ።

1. ከላይ ቁ. 2ን ተመልከት
2. በሕያዋን ምድር በእግዚአብሔር ፊት እሄዳለሁ (ማለትም፣ ያህዌ ይፈውሰዋል/ያድነዋል)
3. መዝ. 116:10-11 በዐውደ-ጽሑፉ ለመተርጎም አስቸጋሪ ነው። እሱም ሊያንጸባርቅ የሚችለው
   ሀ. የወቅቱን እምነት
   ለ. ያለፉት ጽሑፎች (ጳውሎስ መዝ. 116:11ለን ሮሜ. 3:4 ላይ ጠቅሷል)
   እነዚህ ሁለት ቁጥሮች መጥቀስ የሚኖርባቸው የመዝሙረኛውን ነፍስ የሚሹ/የሚያሴሩበትን ነው። እንደዚያ ከሆነ፣ የዚህ መዝሙር ዐውደ-ጽሑፍ ሕመም ሳይሆን ተንኮል/ክህደት ነው (መዝ. 116:11ለ)።
   የLXX የመዝ. 116:10 ትርጉም 2 ቆሮ. 4:13 ላይ ሊታይ ይችላል፣ ነገር ግን ኤምቲ 'ርግጠኛ አይደለም።

**116:11 "በድንጋጤዬ"** *ይህ ቃል ያልተጠናቀቀ አወቃቀር* (ቢዲቢ 342፣ ኬቢ 339) የሚገልጸው የአእምሮ ፍርሃትን ሁኔታ ነው፣ መደናገጥ (መዝ. 31:22)። የመዝ. 116:7 "ዕረፍት" የዚህ ቃል ቀጥተኛ ተቃራኒ ነው!

▣ **"ሰው ሁሉ ሐሰተኛ ነው"** "ዕረፍት" የ "ድንጋጤ" ተቃራኒ እንደሆነ ሁሉ፣ ሐሰተኛ ሰዎችም የያህዌ ተቃራኒ ናቸው (ዘኍ. 23:19ሀ፤1 ሳሙ. 15:29፤ሮሜ. 3:4)።

**መዝሙር ፡116፡12-19**

[12]ስላደረገልኝ ሁሉ
ለእግዚአብሔር ምንን እመልሳለሁ?
[13]የመድኃኒትን ጽዋ እቀበላለሁ፥
የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ።
[14]በሕዝቡ ሁሉ ፊት
ስእለቴን ለእግዚአብሔር እፈጽማለሁ።
[15]የቅዱሳኑ ሞት
በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው።
[16]አቤቱ፥ እኔ ባሪያህ ነኝ፥
ባሪያህ ነኝ፥ የሴት ባሪያህም ልጅ ነኝ
ሰንሰለቴን ሰበርህ።
[17]ለአንተ የምስጋና መሥዋዕትን እሠዋለሁ፥
የእግዚአብሔርንም ስም እጠራለሁ።
[18]በሕዝቡ ሁሉ ፊት
ስእለቴን ለእግዚአብሔር እፈጽማለሁ፥
[19]በእግዚአብሔር ቤት አደባባይ፥
ኢየሩሳሌም ሆይ፥ በመካከልሽም።
ሃሌሉያ

**116፡12-19** ይህ አንጓ ሁሉም ያልተጠናቀቁ አሉት (ከመዝ. 116፡16ሐ በቀር)፣ እሱም በሂደት ላይ ያለውን፣ የሚቀጥለውን አምልኮተ-ጣዖት የሚገልጽ። መዝሙረኛው በመቅደስ አምልኮና በሕይወቱ ምን እንደሚያደርግ ይገልጻል (መዝ. 116፡9) ከያህዌ ታላቅ ክብካቤና ማዳን የተነሣ (መዝ. 116፡12)።

1. የማዳኑን ጽዋ ያነሣል፣ መዝ. 116:13ሀ – ኤቢ (ገጽ 149) የሚለው በመቅደስ የሚደረግ የምስጋና መሥዋዕት አምልኮ ሥርዓት ክፍል ነው፤ እሱም የመጠጥ ቁርባን እንጂ መጠጥ አይደለም (ኒዶቲ፣ ቅጽ. 2፣ ገጽ 618)
2. የእግዚአብሔርን ስም ይጠራል፣ መዝ. 116:13ь፣17ለ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ)
3. ስእለቱን ይፈጽማል፣ መዝ. 116፡14፣18 (ሌዋውያን 27)
4. መሥዋዕት ያቀርባል፣ መዝ. 116፡17
5. ያህዌን በመቅደስ ያመሰግናል፣ መዝ. 116:19 (ዝከ. 116:14) – ይህ ተተኳሪ ከመዝሙር 117 (LXX) መጀመሪያ ጋር የሚሄድ ሊሆን ይችላል

**116:15** "የከበረ" የሚለው ቅጽል (ቢዲቢ 429) ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለከበሩ ነገሮች ነው። በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ላይ የሚገልጸው ሐቅ፣ ያህዌ በጥልቀት እንደሚጠነቀቅ ነው፣ የእርሱ ታማኝ ተከታዮች በዚህ ዓለም ላይ በመከራና በሕመም ውስጥ በሚያልፉበት ሰዓት (መዝ. 72፡14)። እሱ ሁኔታቸውን ጠንቅቆ ያውቃል፣ እናም ፈጥኖ ለዕርዳታ ይመጣል (ዘጸ. 3፡7)።

በወደቀው ዓለም፣ እያንዳንዱ አማኝ በሥጋ ላይድን ይችላል። ውድቀቶች፣ ችግሮች፣ እና ፍራቻዎች ይመጣሉ። ምንም እንኳ የእግዚአብሔርን መገኘት ባናይም፣ እሱ ከእኛ ጋር እና ለእኛ ነው። አንድ ቀን ከእርሱ ጋር እንሆናለን!

ኒዶቲ ቅጽ 2 ገጽ 525 ማስተካከያ (ማረሚያ) ያቀርባል፣ ማለትም "ከ" ("ኤን") የሚለው ፊደል "ሞት" ከሚለው ቃል ላይ ወጥቷል፣ እናም ሥሩ መታየት የሚኖርበት እንደ አራምኛ ቃል "መታመን፣" ነው፣ ብሎም ለስንኙ ማብራሪያ ይሆናል

"በእግዚአብሔር ፊት የከበረ ነው፣ የታማኞቹ እምነት/መታመን።"

ችግሩ ያለው "የከበረ" አጠቃቀም "ከሞት" ጋር መሆኑ ነው። በርግጥ የቅዱሳኑ ሞት የከበረ አይደለም (ማለትም፣ ውድ)። አንዳንድ ሊቃውንት የዕብራይስጡን "የከበረ" (ቢዲቢ 429) ፍች ለውጠውታል ወደ "መሥዋዕትነት ያለው" ወይም "ሥቃይ ያለበት" በሚል። ያህዌን ያሳዝነዋል፣ ታማኝ ተከታዮቹ መከራን ሲቀበሉና ሲሞቱ! የውድቀት አስፈሪ ውጤት ፈጽሞ የእርሱ የፍጥረት አላማ አልነበረም!

▣ **"ቅዱሳን"** መዝ. 16፡10 እና 30፡4 ያለውን ማስታወሻ ድረ-ገጽ ላይ ተመልከት።

**116፡16** "እኔ ባሪያህ ነኝ" የሚለው ለአጽንዖት መደገሙን ተገንዘብ። "ባሪያ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 713) ሰፊ የፍች መስክ አለው፣ እዚህ ግን የሚገልጸው "ምዕመን"ን ይሆናል።

ቀጣዩ መስመር፣ "የሴት ባሪያህ ልጅ" ደግሞ መዝ. 86፡16 ላይ ይገኛል፣ የሚገልጸውም

1. ጻድቅ እናት
2. እስራኤላዊት እናት
3. የትሕትና ፈሊጥ
4. የባርያ ቤተሰብ ወይም የታማኝ ተከታይ ቤተሰብ

መዝሙረኛው ይህንን መደምደሚያ የመሠረተበት ሐቅ ያህዌ (ቢዲቢ 834፣ ኬቢ 986፣ ፒኤል የተጠናቀቀ) ያህዌ ሰንሰለቱን ስለ ሰበረለት ነው (ቢዲቢ 64)፣ ይኸውም ሊገልጽ የሚችለው

1. ለሞት ከሚያደርስ ሕመም ስላዳነው (ከከፋ ሁኔታ ወይም ሲኦል)
2. ከጠላቶች ስላዳነው
3. ከወኅኒ ወይም ግዞት ስላዳነው

4. ከመከራ ስላዳነው ("የከፋ ሁኔታ" የሚለው ቃል [ቢዲቢ 865] መዝ. 116:3 ላይ [ሁለቴ] መዝ. 118:5 እና ሰቆ. 1:3 ላይ ጥቅም ላይ የዋለው ለ"መከራ" ነው)

ይሄንን ቁጥር ለመግለጽ ቀለል ያለው መንገድ "እዚህ አለሁ" ወይም "ለአገልግሎት እገኛለሁ" የሚል ነው። ያህዌ አድኖታል፣ እናም አሁን በፍቃደኝነትና በሙላት ያገለግለዋል (ሮሜ. 12፡1-2)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የዚህን መዝሙር ታሳቢ የሕይወት መቼት አብራራ።
2. ሞትና ሲኦል በሰውኛ ዘይቤ መገለጻቸው ያልተለመደ ነውን?
3. የያህዌን ባሕርያት ዘርዝር።
4. መዝ. 116፡10-11 ለመተርጎም እጅግ አስቸጋሪ የሚሆነው ለምንድነው?
5. ከመዝ. 116፡16 ጀርባ ያለው የብኪ ምናባዊ ምስያ ምንድነው?
6. የመቅደስ አምልኮን የሚያንጸባርቁ ቃላትን፣ ሐረጎችን ዘርዝር።

# መዝሙር 117
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የምስጋና መዝሙር<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም<br>117:1-2 | ሰዎች ሁሉ ጌታን ያመስግኑ<br><br>117:1-2ለ<br>117:2ሐ | ውዳሴ-አምላክ<br><br>117:1-2 | ጌታን ማመስገን<br><br>117:1-2ለ<br>117:2ሐ | ጥሪ ለማመስገን<br><br>117:1-2ለ |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ እጅግ አጭሩ መዝሙር ነው።

ለ. እሱም አሕዛብን ያበረታታል፣ የእስራኤልን አምላክ እንዲያመሰግኑ (መዝሙር 67፤ 100)፣ እውነተኛውን ብቸኛ አምላክ።

ሐ. የእስራኤል አምላክ በሙላት የተገለጸው
1. በፍጥረት ድርጊቱ (ዘፍጥረት 1-2፤ 6-9)
2. ለአብርሃም በሰጠው ተስፋ (ዘፍጥረት 12፤15፤18፤22)
   ሀ. ምድር
   ለ. ዘር
   ሐ. ታላቅ ስም
   መ. የምድር ወገኖች ሁሉ በእርሱ ይባረካሉ
3. ለአብርሃም ዝርዮች የሚደርስ የመዋጀት ድርጊት (መዝ. 117፡2ሀ)
   ሀ. ዘጸአት
   ለ. ድል ማድረግ
   ሐ. ከግዞት መመለስ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡117፡1-2**
**1አሕዛብ ሁላችሁ፥ እግዚአብሔርን አመስግኑት፥**
**ወገኖችም ሁሉ ያመስግኑት**
**2ምሕረቱ በእኛ ላይ ጸንታለችና**
**የእግዚአብሔርም እውነት ለዘላለም ትኖራለች።**
**ሃሌ ሉያ።**

**117፡1** ይህ የሚጀምረውና የሚጨርሰው በፔል ተተኳሪ፣ "አመስግኑ" ነው (ቢ.ዲ.ቢ 237፣ ኬቢ. 248፣ መዝሙር

113፤LXX፣ መዝሙር 116)።

▣ **"አመስግኑት"** ይህ ሁለተኛው ፒኤል ተተኳሪ ነው (ቢዲቢ 986፣ ኬቢ 1387፣ መዝ. 147:12)።

▣ **"አሕዛብም ሁሉ. . .ሕዝቦች ሁሉ"** ይህ ሁለንተናዊ ገጽታ የመዝሙራት ባሕርይ ነው (መዝ. 22:27፤33:8፤47:1፤66:1፣4፤67:3-5፣7፤82:8፤96:7-10፤98:4፤100:1)።

ይህ የብኪ ታላቁ ተልእኮ ነው። እስራኤል "የካህናት መንግሥት" እንዲሆን ነበር (ዘጸ. 19፡5-6) ምድር ሁሉ የእግዚአብሔር ከመሆኑ የተነሣ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

ይህ ቁጥር በጳውሎስ ተጠቅሷል፣ ሮሜ. 15፡11 ላይ፣ እሱም ያህዌ አሕዛብን እንዳካተታቸው አጽንዖት የሚሰጥ፣ በክርስቶስ ሥራ (ሮሜ. 15:9-13፤ራዕ. 7:9 ማስታወሻ)።

**117:2 "ምሕረት. . .እውነት"** እነዚህ የያህዌ ሁለት ባሕርያት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት) ዘወትር አንድ ላይ ነው የሚመዘገቡት (ማለትም፣ መዝ. 108:4፤115:1፤138:2)።

ለ "ምሕረቱ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት (*ሄሴድ*)።

ለ "እውነት" ወይም "ታማኝነት" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ።

▣ **"ለዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም ('ኦላም)።

ይህ ጠቃሚ ነጥብ ነው፣ ከእስራኤል ተደጋጋሚ እምነተ ቢስነት እና ጣዖት አምላኪነት የተነሣ። ያህዌ ለዘላለም ታማኝ ነው፣ ሕዝቡ ግን አይደሉም! እሱ የላቀ ዓላማ አለው፣ ከአንድ ሕዝብ/ብሔር የበለጠ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ያህዌ ለአሕዛብ ያለው ፍቅር፣ ክብካቤ፣ ግድ፣ እና መዋጀት በብኪ እንዴት የተለመደ ነው?
2. *ሄሴድን* አብራራ (ማለትም፣ ምሕረት)።
3. *ኢሚዝን* አብራራ (ማለትም፣ እውነት)። የዚህን መዝሙር ታሳቢ የሕይወት መቼት አብራራ።
4. እግዚአብሔር ለእስራኤል ያለው ፍቅር በአሕዛብ ላይ እንዴት ያለ ተጽዕኖ አሳረፈ?

# መዝሙር 118

## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ምስጋና ለጌታ ስለ ማዳኑ መልካምነት<br><br><u>ኤምቲ መግቢያ የለውም</u> | ምስጋና ለጌታ ስለ ዘላለማዊ ምሕረቱ | ምስጋና በጦርነት ስለ መታደጉ | የምስጋና ጸሎት ለድል | ቀጣይነት ያለው ውዳሴ በዳስ በዓል ላይ |
| 118:1-4 | 118:1 | 118:1 | 118:1-4 | 118:1 |
| | 118:2-4 | 118:2-4 | | 118:2-4 |
| 118:5-9 | 118:5-9 | 118:5-9 | 118:5-9 | 118:5-7 |
| | | | | 118:8-9 |
| 118:10-14 | 118:10-14 | 118:10-14 | 118:10-12 | 118:10-12 |
| | | | 118:13-14 | 118:13-14 |
| 118:15-18 | 118:15-18 | 118:15-18 | 118:15-16 | 118:15-16 |
| | | | 118:17-18 | 118:17-18 |
| 118:19-21 | 118:19-20 | 118:19 | 118:19 | 118:19-21 |
| | | 118:20 | 118:20 | |
| | 118:21 | 118:21-25 | 118:21 | |
| 118:22-29 | 118:22-24 | | 118:22-25 | 118:22-24 |
| | 118:25-28 | | | 118:25-27ለ |
| | | 118:26-27 | 118:26-27 | |
| | | | | 118:27ሐ-28 |
| | | 118:28 | 118:28 | |
| | 118:29 | 118:29 | 118:29 | 118:29 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

*ሀ.* ይህ መዝሙር ምልልስ ያለበት በሂደት ላይ ያለ መዝሙር ነው (መዝ. 118:1 እና 2-4)። በርካታ የተለያዩ ቡድኖች ይገኛሉ እርስ በርሳቸው ምላሽ የሚደራረጉ። ይህም የሚገልጸው
1. ተደጋጋሚ ባሕርዩን
2. በዚህ በዝሙር በርካታ ርዕሰ-ጉዳዮች ተካትተዋል

*ለ.* የዚህ መዝሙር ርግጠኛው ታሪካዊ መቼት አወዛግቧል። ግልጽ የሆነው ነገር የሙሴ የኤርትራ ባሕር ድል ዝማሬ (ማለትም፣ ዘጸአት 15) የዘይቤዎቹ ታሪካዊ ምንጭ ነው። ሆኖም፣ ርግጠኛው ቀን ሊሰማማ የሚችለው ከድኅረ-ግዞት መመለስ ጋር ነው፣ በነህምያ በኩል፣ ወይም የፍጻሜ ዘመናዊ መቼት እሱም መዝሙሩን ተተግባሪ የሚያደርገው፣ ከያንዳንዱ ትውልድ ጫናዎችና ችግሮች ጋር ነው።

ሐ. ከታሪክ አኳያ ይህ መዝሙር ከፋሲካ በዓል ጋር መታወቅ ጀመረ። እሱም ከሀለል መዝሙራት የመጨረሻው ነው፣ መዝሙር 113 እስከ 118። ኢየሱስም ጠቅሶት ነበር፣ በድል አድራጊነት በገባበት ጊዜ (ማቴ. 21:42፤ማርቆስ 12:10፣11፤ሉቃስ 20:17)። ይህ መዝሙር ተዘውትሮ አኪ ላይ ተጠቅሷል፣ የክርስቶስን ሥራ ለመተርጎም (ሐዋ. 4:11፤ሮሜ. 9:32፣33፤ኤፌ. 2:20፤1 ጴጥ. 2:7)።

መ. የአይሁድ ሚድራሽ መዝሙሩን የሚተረጉመው በመሲሐዊ መልኩ ነው። ይህም በተለይ በአኪ አጠቃቀምና ትርጓሜዎች ላይ ይታያል፣ መዝ. 118:22 እና 26 ላይ (ማቴ. 21:9፤23:39፤ማርቆስ 11:9፤ሉቃስ 13:35፤19:38፤ዮሐንስ 12:13)።

ሠ. ይህ መዝሙር በጠባዩ የሚገልጸው የሕዝቡን ልምምዶች ነው፣ በተለዩ ሰዎች አኳያ፣ በዋነኛነትም የእስራኤል ንጉሥ፣ ኋላ ላይ ግን መሲሕ ወደሚል ሁነኛ አካል እየሆነ መጣ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሲሕ)። በዚህ መልኩ፣ እንደ ሁነኛ እስራኤላዊ፣ እሱ ይሄንን ምንባብ ብቻ አልፈጸመም፣ ግን ደግሞ ኢሳይያስ 53ንም ጭምር እንጂ።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡118፡1-4**

**[1]እግዚአብሔርን አመስግኑ፥ ቸር ነውና**
**ምሕረቱ ለዘላለም ናትና።**
**[2]ቸር እንደ ሆነ፥ ምሕረቱ ለዘላለም እንደ ሆነች**
**የእስራኤል ቤት አሁን ይንገሩ።**
**[3]ቸር እንደ ሆነ፥ ምሕረቱ ለዘላለም እንደ ሆነች**
**የአሮን ቤት አሁን ይንገሩ።**
**[4]ቸር እንደ ሆነ፥ ምሕረቱ ለዘላለም እንደ ሆነች**
**እግዚአብሔርን የሚፈሩ ሁሉ አሁን ይንገሩ።**

**118፡1 "አመስግኑ"** ይህ መዝሙር የሚጀምረውና የሚጨርሰው በምስጋና ነው ("አመስግኑ፣" ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል ተተኳሪ*)። ለዚህ መዝሙር የተሻለ ርዕስ የሚሆነው "የምስጋና በዓል" ነው።

የዚህ መዝሙር ግለሰባዊ ትግበራ ለየዕለቱ ሕይወት እንደመሆኑ መጠን፣ እሱ እጅግ ትርጉም ያለው ነው፣ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ያደረገውን በረከት መቁጠር፣ በሁለቱም ከታሪክ አኳያ እና ከተጨባጭ።

▣ **"ጌታ"** ይህ የእግዚአብሔር፣ ያህዌ የኪዳን ስም ነው፣ ከዕብራይስጥ ግሥ፣ "የመሆን ግሥ" (ዘጸ. 3፡14፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች)።

▣ **"መልካም ነው"** ዘወትር አንዱ ብኪን ሲያነብ፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ርግጠኛ አይሆንም (ማለትም፣ ቅዱስ ጦርነት፣ ዘጸአት፣ ግዞቶች)። ይህ መዝሙር የፈጣሪ አምላክን መሠረታዊ ባሕርይ ዳግም ያረጋግጥልናል (1 ዜና. 16:34፤መዝ. 25:8፤34:8፤73:1፤86:5፤100:5፤106:1፤107:1፤118:1፣29፤119:68፤135:3፤136:1፤145:9፤Jer. 33:11)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት።

▣ **"ምሕረቱ ለዘላለም ናትና።"** ይህ የእግዚአብሔርን ምሕረትና ታማኝነት ያሳያል፣ በባሕርዩ ብቻ ሳይሆን፣ ግን ደግሞ በእርሱ የፈጠራና የመዋጀት ድርጊት እንጂ (ነህምያ 9፤ መዝሙር 136)። ይህ ቃል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት [ሄስድ]) በርግጥ የሚለው "የእግዚአብሔርን የኪዳን ታማኝነት" ነው።

**118፡2 "እስራኤል እንዲህ ይበል"** "ይበል" (ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል ተጽዕኗዊ*) ሦስት ጊዜ ተደግሟል። መዝሙር 118:2-4 የሚያሳየው ሦስት የተለዩ ቡድኖችን ነው፣ በእስራኤል ውስጥ፣ እነርሱም ጌታን እንዲያመሰግኑ ጥሪ የተደረገላቸው። እነዚህ ሦስት ወገኖች (ቡድኖች) ደግሞ መዝ. 115፡9-13 ላይ ይታያሉ። ቅደም ተከተሉ ሊሆን የሚችለው፡

1. ሕዝቡ
2. ካህናት
3. እግዚአብሔርን የሚፈሩ (የአይሁድ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 1414፣ የሚለው "ይሁዲነትን የተቀበለ አሕዛብ፣" ነው፣ ነገር ግን መዝሙር 15 የሚለው መልካም እስራኤላዊ ነው)

እነርሱ እግዚአብሔርን ያመሰግናሉ፣ ስለ ኪዳን ታማኝነቱ።

**መዝሙር ፡118፡5-9**

**[5]በተጨነቅሁ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት**
**ሰማኝ አሰፋልኝም።**
**[6]እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፥**
**አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል?**
**[7]እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፥**
**እኔም በጠላቶቼ ላይ አያለሁ።**
**[8]በሰው ከመታመን ይልቅ**

**በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል።**
**9በገዦች ተስፋ ከማድረግ ይልቅ**
**በእግዚአብሔር ተስፋ ማድረግ ይሻላል።**

**118:5 "በተጨነቅሁ ጊዜ እግዚአብሔርን ጠራሁት"** ደራሲው የነበረበት ነባራዊ መቼት የሆነ ዓይነት እስር (እገታ)፣ ስደት፣ ወይም ችግር መሆኑ ግልጽ ነው። ሊሆን የሚችለውም ይህ የአምልኮ መሪ፣ ንጉሥ ቢሆን ወይም በመሲሕ ሰውኛ የሆነ ሕዝብ፣ ችግር ውስጥ ሊገባ ነው።

"መከራ" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ 865) ያልተዘወተረ መልክ ነው፣ እዚህጋ ብቻ የሚገኝ፣ በነጠላ ቁጥር። እሱም በብዙ ቁጥር ሰቆ. 1:3 ላይ እና በአወቃቀር መዝ. 116:3 ላይ ይገኛል (እዚያም አአመመቅ "የሲኦል ጣር" ብሎ የሚተረጉመው)።

▣ **"እግዚአብሔር ሰማኝ፣ በሰፊ ስፍራም አኖረኝ"** ይህ አስደናቂ ማረጋገጫ ነው፣ እግዚአብሔር ዘወትር የዕርዳታ ጥሪያችንን እንደሚሰማና እንደሚመልስ (መዝ. 118:21፤17:6፤31:2፤34:15፤40:1፤69:17፤71:21፤86:1፤102:2)። የዕብራይስጡ ቃል ለ"መከራ" (ቢ.ዲ.ቢ 865) ፍችው "አንዱን ማገት ወይም ጫና ውስጥ ማኖር፣" ነው፣ ዘይቤው ደግሞ "በሰፊ ስፍራ ማኖር" (ቢ.ዲ.ቢ 932) የሚናገረው አንዱን ከእገታ ማውጣትና በሰፊ መሰማርያ ላይ መልቀቅ ነው (መዝ. 4:1፤18:19፤31:8)። አንዳንዶች የሚያስቡት መንግሥት-ሰማያትን እንደሚያመለክት ነው (ኤቢ፣ ገጽ 156)፣ ነገር ግን ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ እሱ የሚለው ከሥጋዊ ችግር ወይም እጦት መዳን ነው።

**118:6 "እግዚአብሔር ረዳቴ ነው፥**
**አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል?"** እንዴት ያለው ብርቱ የእምነት ማረጋገጫ ነው፣ እግዚአብሔር በእኛ ጎን ለመሆኑ (መዝ.16:8፤23:4፤ ኢሳ. 43:1-2)። እናም እግዚአብሔር በእኛ ጎን ከሆነ፣ ድል የተረጋገጠ ነው (መዝ. 56:4፣11)። የእግዚአብሔር መገኘት ታላቁ በረከት ነው!

▣ **"ሰው ምን ያደርገኛል"** ይህ የእምነት ማረጋገጫ ነው፣ የታማኝ ተከታይ፣ እሱም በቅዱስ ቃሉ እና በልምድ፣ የእግዚአብሔርን መገኘት፣ ክብካቤ፣ መጋቢነት፣ እና ጥበቃ የሚያውቅ (መዝ. 56:4፣11፤146:3፤ዕብራውያን 13:6)።

**118:7 "እግዚአብሔር ከእኔ ጋር ነው፣ ከሚረዱኝ ጋር"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ፍችው "እግዚአብሔር የእኛ ወታደራዊ ባለ ድል ነው" የሚል ነው (መዝ. 54:4)። እግዚአብሔር እንደ ተዋጊ ያለው ጽንሰ-ሐሳብ (ኢሳ. 59:17፤ኤፌ. 6:10-12) እጅግ ጠቃሚ ነው፣ ስለ ስሙ ያላግባብ መከራ ስደትን ለሚቀበሉ።

▣ **"እኔም በጠላቶቼ ላይ አያለሁ።"** "በሚጠሉኝ፣" እነርሱም ለመዝሙረኛው "መከራ" ምክንያት የሆኑ፣ መዝ. 118:5፣ የከበቡት 118:10-13።

የእግዚአብሔር ፍርድ ሁለቱንም የፍጻሜያዊ እና ጊዜያዊ ነው። መዝሙራት ዘወትር ይናገራሉ፣ ስለ መከላከልና ፍትሕ፣ በዚህ ሕይወት (መዝ. 23:5፤37:34፤52:5-6፤54:7፤58:10፤59:10፤91:8፤92:11፤112:8)።

**118:8-9 "በሰው ከመታመን ይልቅ**
**በእግዚአብሔር መታመን ይሻላል"** ይህ የጊዜያዊ ድጋፍን ለጥቂት ጊዜ መሆን የሚያረጋግጥ ነው፣ ነገር ግን የዘላለማዊው፣ የሚዋጅ አምላክ ደስታ እና ኃይል (2 ዜና. 32:7-8፤መዝ. 108:12፤146:3፤ኢሳ. 2:22፤30:1-3፤31:1-3፤ኤር. 17:5-8)።

ኤቢ (ገጽ 157) የሚያስረግጠው "ሰው" (አዳም፣ ቢ.ዲ.ቢ 9) መዝ. 118:8 ላይ ከ "አለቃ" ጋር ትይዩ ነው (ቢ.ዲ.ቢ 622) እናም እነርሱ "ሰዎች ሁሉ" ለሚለው ፈሊጥ ነው (ማለትም፣ መዝ. 146:3)።

የአራቱን ቃል ያልተጠናቀቀ አወቃቀር አጠቃቀም ተመልከት።

1. መጠጊያ ይፈልጋሉ – ቢ.ዲ.ቢ 340፣ ኬቢ 337 (ሁለቴ)
2. መታመን – ቢ.ዲ.ቢ 105፣ ኬቢ 120 (ሁለቴ)

## መዝሙር :118:10-14

**10አሕዛብ ሁሉ ከበቡኝ፥**
**በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው**
**11መከበቡንስ ከበቡኝ፥**
**በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው**
**12ንብ ማርን እንዲከብብ ከበቡኝ፥**
**እሳትም በእሾህ ውስጥ እንዲነድድ ነደዱ፥**
**በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው።**
**13ገፋኸኝ፥ ለመውደቅም ተንገዳገድሁ**
**እግዚአብሔር ግን አገዘኝ።**
**14ኃይሌም ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው፥**
**እርሱም መድኃኒት ሆነልኝ።**

**118:10-12 "አሕዛብ ሁሉ ከበቡኝ"** ይህ ሐረግ በበርካታ የተለያዩ መንገዶች ተተርጉሟል።

1. በዚህ መዝሙር ውስጥ ካሉ ብዙ ጠቃሾች እና ሌሎች ቅዱስ ቃላት የተነሣ፣ አንዳንድ ተንታኞች ይሄንን የሚመለከቱት የዘጸአት ጊዜን እንደሚጠቅስ ነው።
2. ብዙ አታቾች የሚገምቱት ግለሰባዊ ገጽታው ከድኅረ ግዞት ጊዜ ጋር የተሻለ ይገጥማል፣ ከኢየሩሳሌም ቅጥሮች ዳግም ከመሠራት ጋር (ነህ. 4:7፤8)።

3. ሌሎች የሚገምቱት ይህ የሚያመለክተው የፍጻሜ ዘመን ዐውድ ነው፣ እዚያም የዚህ ዓለም መንግሥታት የእግዚአብሔርንና የመሲሑን መንግሥት በመቃወም የሚመጡበት (መዝ. 2:2፤ዘካ. 14:2፤ራዕ. 19:11-21)።

▣ **"በእግዚአብሔርም ስም አሸነፍኋቸው"** "እቆርጣቸዋለሁ" (ቢዲቢ 557፣ ኬቢ 555፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ) በጥሬው የዕብራይስጥ ሐረግ ነው፣ ለግዝረት ጥቅም ላይ የሚውል። ከዚህ መዝሙር መሲሐዊ አንድምታ የተነሣ አንዳንዶች ይሄንን የሚመለከቱት ለአሕዛብ ሰዎች መለወጥ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ። ሆኖም፣ ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ የእነርሱ ጥፋት ነው የሚመስለው፣ መዳናቸው ሳይሆን።

የ "እኔ" እና "እኔን" ተደጋጋሚ አጠቃቀም፣ መዝ. 118፡10-13 የሚያመለክተው ደራሲው ንጉሥ መሆኑን ነው። "ከበቡት" ወደ ኢየሩሳሌም ሲል ያለውን ወታደራዊ ስፍራ የሚያመላክት ነው።

**118፡12** እነዚህ ሁለት ዘይቤዎች የሚያመለክቱት የእግዚአብሔር ሕዝብ በጸረ-እግዚአብሔር፣ ዓለማዊ ኃይላት በተመሰቃቀለ ሁኔታ መከበቡንና የእነርሱን (ጠላቶች) ጽኑና ያልታሰበ ጥፋት ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እሳት።

**118:13 "ገፉኸኝ"** ይህ ሐረግ በዕብራይስጥ የተጠናከረ ነው ቢቃል ያልተጠናቀቀ አወቃቀር አጠቃቀምና ቃል የተጠናቀቀ ግሥ ተመሳሳይ ሐረግ (ቢዲቢ 190፣ ኬቢ 218)።

ኤቢ (ገጽ 158) ይሄንን ድርጊት የሚመለከተው እንደ ሞት ፈሊጥ ነው፣ "መሰናከል" ከሚለው ጽንሰ-ሐሳብ ላይ በመመሥረት (መዝ. 35:6፤36:12፤56:13፤116:8፤ማስታወሻ ተመልከት ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 933 ላይ)።

**118:14 "ኃይሌም ዝማሬዬም እግዚአብሔር ነው፥**
**እርሱም መድኃኒት ሆነልኝ።** መዝ. 118:14 እና 15 የድል መዝሙርን ያንጸባርቃሉ፣ እሱም የኤርትራን ባሕር ከተሻገሩ በኋላ የተዘመረ (ዘጸ. 15:2ሀ)፤ተመሳሳይ ጥቅስ ኢሳ 12:2 ላይ ይገኛል።

ለ"ኃይል" ዘጸ. 15:2፤መዝ. 28:8፤46:1፤59:17፤81:1፤ኢሳ. 12:2ለ ተመልከት። ይህ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለወታደራዊ መልክ ነው፣ እንደ "ደኅንነት/መዳን።"

ለ "ደኅንነት" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት (የብኪ ቃል)።

***መዝሙር ፡118፡15-18***

**[15]የእልልታና የመድኃኒት ድምፅ በጻድቃን ድንኳን ነው**
**የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች።**
**[16]የእግዚአብሔር ቀኝ ከፍ ከፍ አደረገችኝ**
**የእግዚአብሔር ቀኝ ኃይልን አደረገች።**
**[17]አልሞትም በሕይወት እኖራለሁ እንጂ፥**
**የእግዚአብሔርንም ሥራ እናገራለሁ።**
**[18]መገሥጽስ እግዚአብሔር ገሥጾኛ**
**ለሞት ግን አልሰጠኝም።**

**118፡15 "የእልልታና የመድኃኒት ድምፅ"** ዘጸአት 15፡6፣12 ተመልከት።

▣ **"የጻድቃን ድንኳኖች"** ይህ ታሪካዊ ጠቃሽ ነው (ወይም የሙት ዘይቤ) በምድረ-በዳ የመዞር ዘመን፣ እሱም ዘወትር በእስራኤል ወግ የሚነሣ፣ በእግዚአብሔር እና በሕዝቡ መካከል ባለው የፍርድ ቤት ክርክር።

**118:15-16 "የእግዚአብሔር ቀኝ"** ይህ ሦስት ጊዜ የተደገመ ሐረግ አጽንዖት የሚሰጠው ሰውኛ (አንትሮፖሞርፊክ) ቃላትን ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሲገለጽ) ኃይል፣ መገኘት፣ እና የእግዚአብሔር ፍቃደኝነት፣ በሕዝቡ ጎን ለመሥራት በጊዜና በዘላለማዊነት። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ።

"ግራ እጅ" የሚለው ቃል ድካምን የሚገልጽ ነው፣ እናም ለእግዚአብሔር ድርጊት ፈጽሞ ጥቅም ላይ ውሎ አያውቅም።

**118:17 "አልሞትም በሕይወት እኖራለሁ"** ይህ ለብሔራዊ መዳን አጽንዖት ሊሆን ይችላል፣ ነገር ግን ጥቅም ላይ የዋለው በአንድ ግለሰብ ሁኔታ ነው።

▣ **"የእግዚአብሔርንም ሥራ እናገራለሁ።"** ይህ የሚያመለክተው በመቅደስ የሚሆን የቃል ምስጋና ነው (መዝ. 9፡14)። ይህ ሁለቱንም መግለጫ መንገድ ነው

1. ከሥነ-መለኮት አኳያ ስለ ያህዌ (ዘጸ. 9:16፤መዝ. 96:1-6)
2. በያህዌ የግል መታመን (ዘጸ. 10:2)

ግሡ (ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765፣ ፒኤል ያልተጠናቀቀ) የሚገልጸው የያህዌን የማዳን ሥራ ዳግመኛ መናገር ነው (መዝ. 40:5፤73:28፤78:3፣4፤79:13፤107:22)። ይህ የያህዌን ሥራ ዳግም መግለጽ

1. ቀጣዩን ትውልድ ታማኝ ተከታዮች ያስተምራል (ዘዳ. 4:9፣10፤6:7፣20-25፤11:19፤31:13፤32:46)
2. ለአሕዛብ ወንጌልን ያደርሳል (ዘዳ. 4:6)

**118:18 "መገሥጽስ እግዚአብሔር ገሥጾኛ"** ይህ የሚያመለክተው፣ የእግዚአብሔር ሕዝብ እዚህ ተምሳሌታዊ የሆነው፣ እንደ አንድ ግለሰብ ሲሆን፣ በጽኑ መከራ ውስጥ ያልፋል፣ ከኃጢአታቸውና ካለመታመናቸው የተነሣ። እሱም ደግሞ አጽንዖት የሚሰጥ ነው፣ እግዚአብሔር ታሪክን

ለመቆጣጠሩ ሐቅ። እነዚህ ነገሮች ትርጉም የሌላቸው ሁነቶች አይደሉም፣ ነገር ግን ታሪካዊ ዓላማ አላቸው፣ ወደ እግዚአብሔር ድል መዳረሻ መደምደሚያ የሚያመራ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

የግለሰባዊና የተጠቃለለ ገጽታዎች ሊታዩ የሚችሉት

1. የሁለት ነጠላ ቁጥር ያልተጠናቀቁዎች በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ መዋል መዝ. 118:19፣28 ላይ
2. የሁለት የብዙ ቁጥር ተጓዳኞች መዝ. 118:24 ላይ ጥቅም ላይ የዋሉ፣ ሂፊል የብዙ ቁጥር ተተኳሪ 118:29 ላይ ተመልከት

ደግሞም "መገሠጽስ ገሠጸኝ" የሚለውን ተመልከት ያልተወሰነ ፍጹም እና የተጠናቀቀ ግሥ መሆኑን፣ ከተመሳሳይ ሥር (ቢዲቢ 415፣ ኬቢ 418)፣ እሱም ጽኑነትን የሚገልጽ (ተመሳሳይ መልክ ግን የተለያየ ሥር መዝ. 118:13)።

እግዚአብሔር ልጆቹን ይገሥጻል (ዘዳ. 4:36፤8:5፤2 ሳሙ. 7:14፤ኢዮብ 5:17፤33:19፤መዝ. 73:14፤94:12፤119:67፣71፣75፤ምሳ. 3:11-12፤ኤር. 31:18፤1 ቆሮ. 11:32፤ዕብ. 12:5-11፤ራዕ. 3:19)።

**መዝሙር ፡118፡19-21**

**19የጽድቅን ደጆች ክፈቱልኝ**
**ወደ እነርሱ ገብቼ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።**
**20ይህች የእግዚአብሔር ደጅ ናት**
**ወደ እርስዋ ጻድቃን ይገባሉ።**
**21ሰምተኸኛልና፥**
**መድኃኒትም ሆነኸኛልና አመሰግንሃለሁ።**

**118:19 "የጽድቅን ደጆች ክፈቱልኝ"** "ክፈቱልኝ" (ቢዲቢ 834፣ ኬቢ 986 *ቃል ተተኳሪ* ነው። መዝሙር 118:19-27 ስለ ጉዞ የሚናገር ይመስላል (ወታደራዊ ሊሆን ይችላል) ከኢየሩሳሌም ከተማ ውጭ ወደ መቅደሱ ስፍራ ውስጥ። መዝሙር 118:19 መቅደስን የሚገልጽ አይደለም፣ እሱም 118፡26፣27 ላይ ተለይቶ የተጠቀሰው፣ ነገር ግን የኢየሩሳሌም ከተማ በር።

**118:20 "ወደ እርስዋ ጻድቃን ይገባሉ።"** ይህ የአጀብ ጉዞ ወደ ቅዱስ አካባቢ ሲገባ ነው፣ ወደ ከተማ ወይም መቅደስ። የጻድቅነት መለኪያው ብሔራዊ ወይም የተጠቃለለው ብቻ አይደለም፣ ግን ደግሞ ግለሰብም እንጂ (መዝ. 15:1-2፤24:3-6፤26:6፤140:13፤ኢሳ. 33:13-16)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ።

**118:21 "መድኃኒትም ሆነኸኛልና"** አንዱ ማስታወስ የሚገባው "ደኅንነት" የሚለው ቃል (መዝ. 118፡14) በብኪ የሚናገረው ሥጋዊ (አካላዊ) ትድግናን ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት (የብኪ ቃል)።

**መዝሙር ፡118፡22-29**

**22ግንበኞች የናቁት ድንጋይ፥**
**እርሱ የማዕዘን ራስ ሆነ፥**
**23ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፥**
**ለዓይናችንም ድንቅ ናት።**
**24እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት**
**ሐሤትን እናድርግ፥ በእርስዋም ደስ ይበለን።**
**25አቤቱ፥ እባክህ፥ አሁን አድን**
**አቤቱ፥ እባክህ፥ አሁን አቅና።**
**26በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው**
**ከእግዚአብሔር ቤት መረቅናችሁ።**
**27እግዚአብሔር አምላክ ነው፥ ለእኛም በራልን**
**እስከ መሠዊያው ቀንዶች ድረስ የበዓሉን መሥዋዕት በገመድ እሰሩት።**
**28አንተ አምላኬ ነህ አመሰግንሃለሁ።**
**አንተ አምላኬ ነህ፥ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ**
**ሰምተኸኛልና፥ መድኃኒትም ሆነኸኛልና አመሰግንሃለሁ።**
**29እግዚአብሔርን አመስግኑ፥ ቸር ነውና**
**ምሕረቱ ለዘላለም ናትና።**

**118:22 "ግንበኞች የናቁት ድንጋይ"** ይህ በግልጽ በአያዎ ዘይቤ ጥቅም ላይ የዋለ ነው። እሱም እዚህጋ የሚያመለክተው ብሔራዊ መተውን (መናቅን) ነው። ነገር ግን ከክርስቶስ ሕይወት እንደምንረዳው በግለሰብ ደረጃ በእርሱ እንደተፈጸመ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የማዕዘን ድንጋይ።

▣ **"የማዕዘን ድንጋይ ሆነ"** ይህ መሲሑን የሚያመለክት ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሲሕ)፣ ኢሳ. 28፡16 ላይ ጥቅም ላይ የዋለ። እሱም ደግሞ ስለ መሲሑ መናቅ የሚናገር እና የእግዚአብሔር ዓላማ ሽንፈት ሊመስል ይችላል (ማለትም፣ ቀራንዮ)።

**118:23 "ይህች ከእግዚአብሔር ዘንድ ሆነች፥**

***ለዓይናችንም ድንቅ ናት።"*** የእግዚአብሔር መንገድ ከእኛ መንገድ እጅግ ይለያል (ኢሳ. 55፡9-11)። ማንም መሲሑ ሥጋ የለበሰ አምላክ ነው ብሎ አልጠበቀም። ማንም የእርሱን ተቀያሪ መሥዋዕትነት አልጠበቀም (ኢሳይያስ 53፤ማርቆስ 10:45፤2 ቆሮ. 5:21)። ነገር ግን ይህ የእግዚአብሔር ቀድሞ ያተሰበበት ዕቅድ ነበር (ሐዋ. 2:23፤3:18፤4:28)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

**118:24 "እግዚአብሔር የሠራት ቀን ይህች ናት**

***ሐሤትን እናድርግ፥ በእርስዋም ደስ ይበለን።"*** እግዚአብሔር ታሪክን ይቆጣጠራል (በሁለቱም በአጠቃላይም ሆነ በግለሰብ ደረጃ)! ያ ማለት መንፈሳዊ ጥፋት ዘወትር ወደ ታላቅ መንፈሳዊ ድል ይቀየራል!

በሀናህ ዊዛል ስሚዝ፣ *የደስተኛ ሕይወት የክርስቲያን ምሥጢር* የሚለውን መጽሐፍ እጠቁማለሁ።

▣ ለ "ቀን" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቀን (ዮም)።

**118:25 "አቤቱ፥ እባክህ፥ አሁን አድን"** ይህ "ሆሳዕና" የሚለው ቃል ነው፣ ይኸውም ስለ ኢየሱስ የተባለ፣ በድል አድራጊነት ወደ ኢየሩሳሌም ሲገባ፣ በምድራዊ ሕይወቱ የመጨረሻ ሳምንት (ማቴ. 21፡42፤45)። የዚህ መዝሙር ዋነኛ ታሪካዊ መቼት ምንም ይሁን፣ በአንደኛው ክፍለ-ዘመን ራቢያዊ ይሁዲነት እንደ እንኳን ደኅና መጣችሁ ክብረ-በዓል ጥቅም ላይ ውሎ ነበር፣ ለፋሲካ ወደ ከተማይቱ ለሚገቡ ተጓዦች (መናኞች)። ሆኖም፣ ኢየሱስ በመጣ ጊዜ፣ እነርሱ ያንን ዓመታዊ ሰላምታ ወስደው ለእርሱ ለግሉ አደረጉት።

ይህ ቁጥር በሁለት ተተኳሪዎች ይጀምራል።

1. ማዳን – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ ሂፊል
2. ብልጽግናን ላክ – ቢዲቢ 852 II፣ ኬቢ 1026፣ ሂፊል

በብኪ ሥነ-መለኮት (ማለትም፣ "ሁለቱ መንገዶች፣" ዘዳ. 30:15፣19፤መዝ 1)፣ የእግዚአብሔር ይቅርታ እና መቀበሉ ይገለጽ የነበረው በሚታይ መልኩ በብልጽግና ነበር። ሆኖም፣ ይህ ሁልጊዜ ምክንያቱ እንደሆነ አያረጋግጥም (ኢዮብ፣ መዝሙር 73)።

**118:26 "በእግዚአብሔር ስም የሚመጣ ቡሩክ ነው"** የዚህ ሐረግ የአኪ አጠቃቀም ለዚህ ሃለል መዝሙር መሲሐዊ ገጽታ ያስቀምጣል (ማቴ. 21:9፤23:39፤ማርቆስ 11:9፤ሉቃስ 13:35፤19:38፤ዮሐንስ 12:13)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሲሕ።

**118:27**

**አአመመቅ፣ አየተመቅ፣**

**አእቅ፣ ጄፒኤስኦኤ "እግዚአብሔር አምላክ ነው"**

**አኪጀቅ "አምላክ እግዚአብሔር ነው"**

ምንም ግሥ የለም፣ ኤል ብቻ(ቢዲቢ 42) እና ያህዌ (ቢዲቢ 217)። ይኸው ተመሳሳይ መልክ መዝ. 85:9 ላይ ይገኛል። ተመሳሳይ ቅንብር ያለ ግሥ ደግሞ መዝ. 118:28 ላይ ይገኛል፣ ኤል ("የእኔ ኤል") እና ተውላጠ ስም (ቢዲቢ 61)።

የእስራኤል መለኮት (አምላክ) በበርካታ ስሞች ይጠራል

1. አንዳንዶቹ በታሪክ ውስጥ እየዳበሩ የመጡ ናቸው
2. አንዳንዶቹ የጣዖት አማልክት መጠሪያ የነበሩና ለእስራኤል አምላክ ጥቅም ላይ የዋሉ ናቸው
3. አንዳንዶቹ የእርሱን ሕላዌ የተለያዩ ገጽታዎች የሚገልጹ ናቸው
4. አንዳንዶቹ ቅኔአዊ ትይዩ ናቸው፣ ለጽሑፋዊ ዓላማ

▣ **"ለእኛም በራልን"** በርካታ ትርጉሞች ይገኛሉ።

1. የእግዚአብሔር አካላዊ መገኘት — 89:15፤90:8
2. የእግዚአብሔር ራዕይ (መገለጥ)
   ሀ. ቅዱስ ቃሉ መዝ. 19:8፤36:9፤119:105፤ኢሳ. 51:4
   ለ. መሲሕ – ኢሳ. 49:6፤ሚክ. 7:8፤ዮሐንስ 1:9፤3:19-21፤12:35-36፤1 ዮሐንስ 2:8
3. የእግዚአብሔር ባርኮት – ዘኁ. 6:25
4. ሼክናህ የዘጸአት ደመና – ዘጸ. 13:21-22፤14:20
5. የእግዚአብሔር ተንቀሳቃሽ ዙፋን ሠረገላ – ሕዝ. 1:4፤27

▣ **"እስከ *መሠዊያው* ቀንዶች ድረስ የበዓሉን *መሥዋዕት* በገመድ እሰሩት።"** ይህ እጅግ አስቸጋሪ የዕብራይስጥ ሐረግ ነው፣ እናም በተለያዩ በርካታ መንገዶች ነው መረዳት ያገኘው።

1. "የመናኞች አንድ ላይ መሆን" — ይህ የጽሑፉን መታረም ያካትታል፣ በሙት ባሕር ጥቅሎች ላይ በመመሥረት።
2. "ዝንጣፊዎችን በእጃችሁ በመያዝ በአጀብና በሰልፍ በመሆን" — ይህ የኢየሩሳሌም መጽሐፍ ቅዱስ (ኢመቅ) እና አኢቅ ትርጉም ነው፤ እሱም የሚያመለክተው የብኪን ጠቃሽ ነው፣ ለማደሪያው ድንኳን (የዳስ) በዓል ጥቅም ላይ የሚውሉትን ዝንጣፊዎች (ቅርንጫፎች) (ሌዋ. 23፡40)። "ገመድ" የሚለው ቃል ለዝንጣፊዎች ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል (ሕዝ. 19:11፤31:3፤10፤14)።
3. "እስከ *መሠዊያው* ቀንዶች ድረስ *መሥዋዕቱን* አቅርቡት።" — ይህ ከዐውደ-ጽሑፉ ጋር በተሻለ የሚገጥም ይመስላል፣ "እሰሩት" የሚለው ቃልም በዚህ ትርጉም ሊገኝ ይችላል መሳ. 15:13፤16:11፤ሕዝ. 3:25 ላይ።
4. የመሥዋዕት ጽንሰ-ሐሳብ የተያዘው በክርስቶስ ተቀያሪ *መሥዋዕትነት* ነው (ማለትም፣ ኢሳ. 52፡13-53፡12)፣ እሱም በማሶረቲክ ጽሑፍ ሚል. 2፡3 ላይ የተጠቀሰ። የመሠዊያው ቀንዶች የመሠዊያው እጅግ ቅዱስ ስፍራ ነው፣ በዚያም የመሥዋዕቱ ደም የሚያርፍበት (ዘጸ. 27:2፤30:10፤ሌዋ. 4:7፣18፣ 25፣30፣34፤8:15፤9:9፤16:18)።

**118፡28-29** ይህ መዝሙር የሚጨርሰው እንደ አጀማመሩ ነው፣ በምስጋና በዓል (ማለትም፣ ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ ሂፊል ተተኳሪS) ለእግዚአብሔር ስለ ማንነቱ፣ ስላደረገው፣ እና ወደፊትም ከታማኝ ተከታዮቹ አኳያ ስለሚያደርገው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ሁሉንም የእግዚአብሔር በረከቶች በዚህ መዝሙር ላይ ለእኛ የተሰጡንን ዘርዝር።
2. ብዙ ሊቃውንት ይህ መዝሙር የተለያዩ ምልልሶች ስብስብ ነው ብለው ለምን ያስባሉ?
3. ሕዝቡ በሰውኛ ዘይቤ በንጉሥ እና ኋላም በመሲሕ እንዴት ተመሰለ?
4. መሲሐዊ ይዘቶችን ግለጽ፣ መዝ. 118:22 እና 26 ላይ ያሉትን፣ ከጥንታዊ እስራኤል ጋርም እንዴት እንደሚገጥም እና ከክርስቶስ ሕይወት ጋር እንዴት እንደሚገጥም።
5. የመዝ. 118፡27 ተመራጩ ትርጉም ምንድነው? የእርሱስ አንድምታዎች ምንድናቸው፣ ከናዝሬቱ ኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ጋር?

# መዝሙር 119
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ምልጃና ጸሎት ከእግዚአብሔር ሕግ ጋር የተያያዙ<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | ምልጃ ስለ እግዚአብሔር ቃል ግሩምነት | ምልጃ ስለ እግዚአብሔር ቃል | የእግዚአብሔር ሕግ | መለኮታዊውን ሕግ ስለ ማመስገን |
| 119:1-8<br>(አሌፍ) | 119:1-8 | 119:1-8 | 119:1-8<br>ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዝ<br>119:9-16 | 119:1-8 |
| 119:9-16<br>(ቤት) | 119:9-16 | 119:9-16 | ደስታ በእግዚአብሔር ሕግ<br>119:17-24 | 119:9-16 |
| 119:17-24<br>(ጋሜል) | 119:17-24 | 119:17-24 | የእግዚአብሔርን ሕግ ለመታዘዝ ቁርጠኝነት<br>119:25-32 | 119:17-24 |
| 119:25-32<br>(ዳሌጥ) | 119:25-32 | 119:25-32 | ጸሎት ለማስተዋል<br>119:33-40 | 119:25-32 |
| 119:33-40<br>(ሄ) | 119:33-40 | 119:33-40 | የእግዚአብሔርን ሕግ መታመን<br>119:41-48 | 119:33-40 |
| 119:41-48<br>(ዋው) | 119:41-48 | 119:41-48 | በእግዚአብሔር ሕግ መታመን<br>119:49-56<br>ለእግዚአብሔር ሕግ መሰጠት<br>119:57-64 | 119:41-48 |
| 119:49-56<br>(ዛይ) | 119:49-56 | 119:49-56 | የእግዚአብሔር ሕግ ዋጋ<br>119:65-72 | 119:49-56 |
| 119:57-64<br>(ሔት) | 119:57-64 | 119:57-64 | የእግዚአብሔር ሕግ ፍትሐዊነት<br>119:73-80 | 119:57-64 |
| 119:65-72<br>(ጤት) | 119:65-72 | 119:65-72 | ጸሎት ለመዳን<br>119:81-88 | 119:65-72 |
| 119:73-80<br>(ዮድ) | 119:73-80 | 119:73-80 | እምነት በእግዚአብሔር ሕግ<br>119:89-96 | 119:73-80 |
| 119:81-88<br>(ካፍ) | 119:81-88 | 119:81-88 | የእግዚአብሔር ሕግ ፍቅር<br>119:97-104<br>ብርሃን ከእግዚአብሔር ሕግ<br>119:105-112 | 119:81-88 |
| 119:89-96<br>(ላሜድ) | 119:89-96 | 119:89-96 | ደኅንነት በእግዚአብሔር ሕግ<br>119:113-120 | 119:89-96 |
| 119:97-104<br>(ሜም) | 119:97-104 | 119:97-104 | ለእግዚአብሔር ሕግ መታዘዝ<br>119:121-128 | 119:97-104 |
| 119:105-112<br>(ኖን) | 119:105-112 | 119:105-112 | የእግዚአብሔርን ሕግ የመጠበቅ ፍላጎት<br>119:129-136 | 119:105-112 |
| 119:113-120<br>(ሳምኬት) | 119:113-120 | 119:113-120 | የእግዚአብሔር ሕግ ፍትሐዊነት<br>119:137-144 | 119:113-120 |
| 119:121-128<br>(ዔ) | 119:121-128 | 119:121-128 | ጸሎት ለደኅንነት<br>119:145-152 | 119:121-128 |
| 119:129-136 | 119:129-136 | 119:129-136 | ልመና ለዕርዳታ<br>119:153-160 | 119:129-136 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| (ፌ) | | | ለእግዚአብሔር ሕግ የተሰጠ<br>119:161-168 | |
| 119:137-144<br>(ጻዴ) | 119:137-144 | 119:137-144 | የዕርዳታ ጸሎት<br>119:169-176 | 119:137-144 |
| 119:145-152<br>(ቆፍ) | 119:145-152 | 119:145-152 | | 119:145-152 |
| 119:153-160<br>(ሬስ) | 119:153-160 | 119:153-160 | | 119:153-160 |
| 119:161-168<br>(ሳን) | 119:161-168 | 119:161-168 | | 119:161-168 |
| 119:169-176<br>(ታው) | 119:169-176 | 119:169-176 | | 119:169-176 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

I. የመግቢያ መግለጫ

መጽሐፍ ቅዱስን እንደሚወድና ሕይወቱንም እሱን በማጥናት እንደሚያሳልፍ ሰው፣ ይህ መዝሙር የተለየ መዝገብ (ሀብት) ነው (እንደ መዝሙር 19)። መጽሐፍ ቅዱስ፣ የተጻፈ የእግዚአብሔር ቃል፣ የእግዚአብሔርን ሕያው ቃል፣ ኢየሱስን እንዳውቅ ፈቅዶልኛል (አስችሎኛል) (ዮሐንስ 1:1-14፤ፊሊ. 2:6-11፤ቆላ. 1:13-16፤ዕብ. 1:2-3)። የመንፈስ ቅዱስ ማብራራት (ብርሃን) እዝራ እንዳደረገው እንዳደርግ አስችሎኛል (ዕዝራ 7:10)። መዝሙር 119 በርግጥ
ሀ. በረከት ነው፣ መዝ. 119:1
ለ. የሕይወት ስልት እምነት ነው፣ መዝ. 119:1-2
ሐ. ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው፣ መዝ. 119:105
በታላቅ ደስታ፣ ሰላም፣ እና ተስፋ አበረክትላችኋለሁ፣ እሱም በተሳካ ሁኔታ እንዲፈጥር
ሀ. መጽሐፍ ቅዱስን የማጥናት ፍላጎት
ለ. መጽሐፍ ቅዱስን የመኖር ፍላጎት
ሐ. ጥልቅ የሆነ ግላዊ ግንኙነት በሦስትነቱ አንድ ከሆነ አምላክ ጋር

አንድ ተጨማሪ ማብራሪያ ይሄንን ረጅም መዝሙር እንዴት እንደምይዘው። እሱ እጅግ ረጅም እና ተደጋጋሚ ነው፣ ስለዚህም በእያንዳንዱ አንጓ ላይ ለማየት ወሰንኩ (ማለትም፣ እያንዳንዱን ተከታታይ ፊደል፣ ከዕብራይስጥ የፊደል ገበታ)። በእያንዳንዱ ምድብ የተለየ ባሕርይ ላይ ለመሥራት ሞክሬአለሁ፣ እናም ሁሉን አቀፍ ማጠቃለያ ሳይሆን።

II. ታሪካዊ መቼት

ሀ. የዓረብኛው ትርጉም ዳዊትን እንደ ደራሲ ያስቀምጠዋል።

ለ. ዳሆድ *በመልኅቅ በጽሐፍ ቅዱስ ኮሜንተሪ* ላይ፣ የሚያስረግጠው የተባበረው መንግሥት (ሳኦል-ሰሎሞን) ጊዜ እጅግ ሊሆን የሚችል ነው። እሱም ወደዚህ የመጣው
1. ይሄንን መዝሙር ከትርጉሙ ጋር በማነጻጸር ነው፣ በሙት ባሕር ጥቅሎች ከተገኙት መካከል፣ እና
2. ይህ መዝሙር ብዙ ቅድመ-ግዞት ይዘቶችን ይዟል።

ሐ. ሌዎፖልድ መቼቱን የሚመለከተው እንደ ድኅረ-ግዞት ነው (ዕዝራ፣ ነህምያ፣ ሐጌ፣ ሚልክያስ)። ይሄንንም መሠረት ያደረገው በ፡

1. ከዳግመኛ መስፈር እና ከስደት ጋር የተያያዙት ችግሮች፣ እነርሱም ተዘውትረው መዝሙራት ላይ የተጠቀሱ
2. የመሥዋዕት ሥርዓቱ ምንም አለመጠቀስ፣ እንደ መቅደሱና የአምልኮ ሥርዓቱ መቅረት እንደሆነ እንዲያምን አድርጎታል፣ እየጨመረ ከመጣው የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ጋር፣ እጅግ በተሻለ ሊገጥም የሚችለው ፊተኛው ድኅረ-ግዞት መቼት ነው።

መ. የዚህ መዝሙር ሁነት ደስታ ነው (መዝ. 119፡14፤16፤24፤35፤47፤70፤77፤92፤111፤143፤ 162፤174) እናም በእግዚአብሔርና በገለጠው እውነት መታመን ነው፣ በመከራ መካከል። ይህ እውቀት ሰላምና ጽናትን ያመጣል።

III. ጽሑፋዊ ይዘቶች

ሀ. ይህ፣ እንደ መዝሙር 9-10፤25፤34፤37፤111፤112፤እና 145 መስቀልያ ነው፣ በሃያ ሁለቱ የዕብራይስጥ ፊደላት ላይ በመመሥረት። ይኸው ተመሳሳይ ቅርጽ ምሳ. 31፡10-31 ላይ እና ሰቆቃወ የመጀመሪያዎቹ አራት ምዕራፎች ላይ ይገኛል። ይኸም እጅግ ረጅሙና እጅግ በጣም የዳበረው መስቀልያ ነው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ። እያንዳንዱ የዕብራይስጥ ፊደል ስምንት ቁጥሮችን ይጀምራል።

ለ. በዚህ መዝሙር ላይ ተደጋጋሚ ጭብጥ በእያንዳንዱ ቁጥር ላይ ይገኛል፣ ከእግዚአብሔር ትምህርቶች ጋር በተያያዘ፣ ለሰው ልጆች። መዝሙረኛው በርካታ ተመሳሳዮችን ይጠቀማል፣ ለሕግ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ለእግዚአብሔር ራዕይ (መገለጥ) ቃላት፣ መዝ. 19፡7-9)፡

1. ሕግ — 25 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
2. ምስክሮች — 23 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
3. ሐሳቦች — 21 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
4. ደንቦች — 20 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
5. ትእዛዛት — 22 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
6. ፍርዶች — 23 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
7. ቃል — 24 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
8. ቃላት — 19 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
9. መንገድ — 13 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
10. እውነት ወይም ታማኝነት — 5 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል
11. ጽድቅ — 14 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል

ሐ. ኪምቺ (ማለትም፣ የአይሁድ ኮሜንታተር፣ 1160 – 1235 ዓ.ም) የተመሳሳይ መግለጫ (ፍች)፣ እግዚአብሔር ለሰው ስላደረገው መገለጥ (ራዕይ)፡

1. ሕግ — "ተግባራትን ማደራጀትና፣ እንዴት እንደሚተገበሩ የሚያሳይ ነው"
2. ምስክርነቶች — "ሐሳቦች እነርሱም ለምስክርነት ወይም ለብሔራዊ ተግባቦት"
3. ሐሳቦች — ጥቅም ላይ የሚውሉት "ሐሳቦች ይኸውም ምክንያታዊ ሐሳብ የሚያስተምረው፣ በተፈጥሯችን የሚዳብረው"
4. ደንቦች — "ሐሳቦች፣ ምክንያታዊ አስተሳሰብ የማይታወቅበት"
5. ፍርዶች — "ፍርዶች፣ በሰው እና በባልንጀራው መካከል የሚያልፉ"
6. መንገድ — "መንገድ፣ ቅዱስ ቃሉ መሠረት የያዘበት ሕግ (ደንብ) ነው"

መ. የእግዚአብሔር ራዕይ እና የእግዚአብሔር አካል በዚህ መዝሙር ላይ ተዋህደዋል። የእግዚአብሔርን ራዕይ ማወቅ ማለት እሱን ማወቅ ነው። ከእግዚአብሔር ራዕይ ጋር መጣበቅ፣ ከእርሱ ጋር መጣበቅ ነው (ማለትም፣ መዝ.119፡31ሀን ከዘዳ. 10፡20 ጋር አነጻጽር)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡119፡1-8 (አሌፍ)**

**1በመንገዳቸው ንጹሐን የሆኑ፥**
**በእግዚአብሔርም ሕግ የሚሄዱ ምስጉኖች ናቸው።**
**2ምስክሩን የሚፈልጉ፥**
**በፍጹም ልብ የሚሹት ምስጉኖች ናቸው**
**3ዓመፅንም አያደርጉም፥**
**በመንገዶቹም ይሄዳሉ።**
**4ትእዛዛትህን እጅግ እንጠብቅ ዘንድ**

**አንተ አዘዝህ።**
**[5]ሥርዓትህን ለመጠበቅ**
**መንገዶቼ ይቀኑ ዘንድ እወድድ ነበር።**
**[6]ትእዛዝህን ሁሉ ስመለከት**
**በዚያን ጊዜ አላፍርም።**
**[7]አቤቱ፥ የጽድቅህን ፍርድ ስማር**
**በቅን ልብ አመሰግንሃለሁ።**
**[8]ሥርዓትህን እጠብቃለሁ**
**በፍጹም አትጣለኝ።**

**119፡1** ይህ አንጻ "የተባረከ"ን ይገልጻል (ቢ.ዲ.ቢ. 80፣ መዝ. 1፡1፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: ባርኮት [ብኪ])።

1. በመንገዳቸው (ማለትም፣ በሕይወት ስልት) ንጹሐን የሆኑ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ነውር የሌለው፣ ንጹሕ፣ በደል የሌለው፣ ነቀፋ የሌለበት)፣ መዝ. 119፡1ሀ
2. በእግዚአብሔርም ሕግ የሚሄዱ — የታዛዥነት የሕይወት ስልትን መግለጫ ሌላው መንገድ፣ መዝ. 119፡1ለ፣ 3ለ
3. ምስክሩን የሚፈልጉ፣ መዝ. 119፡2ሀ
4. በፍጹም ልብ የሚሹት፤ መዝ. 119፡2ለ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ)፣ መዝ. 9:10፤14:12 (እና ሕጉን የሚፈልጉ፣ መዝ. 119:45፣94፣ 155)
5. ምንም በደል የማይፈጽሙ፣ መዝ. 119:3ሀ
6. የእግዚአብሔርን ኪዳን የሚጠብቁ፣ መዝ. 119:4ለ፣5ለ፣8ለ
7. ሥርዓቱን የሚጠብቁ፣ መዝ. 119:8ሀ

የእግዚአብሔርን ራዕይ ለማወቅ እና ከዚያም እሱን ለመጠበቅ የተሰጠውን አጽንዖት ተገንዘብ! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ።

▣ በርካታ ቃላት አሉ የእግዚአብሔርን ራዕይ የሚገልጹ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ)።

1. ሕግ (ቢ.ዲ.ቢ. 435)፣ መዝ. 119:1ለ
2. ምስክርነቶች (ቢ.ዲ.ቢ. 730)፣ መዝ. 119:2ሀ
3. መንገዶች (ቢ.ዲ.ቢ. 202)፣ መዝ. 119:3b፣ 5ሀ
4. ሐሳቦች (ቢ.ዲ.ቢ. 824)፣ መዝ. 119:4ሀ
5. ሥርዓቶች (ቢ.ዲ.ቢ. 349)፣ መዝ. 119:5ለ፣ 8ሀ
6. ትእዛዛት (ቢ.ዲ.ቢ. 846)፣ መዝ. 119:6ለ
7. ፍርዶች (ቢ.ዲ.ቢ. 1048)፣ መዝ. 119:7ለ

ደግሞም፣ እያንዳንዱ ቁጥር በዚህ ረጅም መስቀልያ መዝሙር ላይ ከእነዚህ አንዱን ይጠቅሳል (ወይም ሌሎች በርካቶችን፣ ለአብነትም "ቃል" መዝ. 119:9፣11፣16 ላይ፣ ወይም "ትእዛዛት፣" መዝ. 119:13፣30፣39፣43፣ 52፣62፣75፣84፣102፣106፣120፣137፣147፣149፣156፣ 160፣164፣175)።

**119:2 "መመልከት"** ይህ የመልካም አኗኗር ቁልፍ ገጽታ ነው። እሱም በብዙ ነገሮች ጥቅም ላይ ይውላል።

1. ሥርዓቱን መጠበቅ – መዝ. 119:2፤22፤129
2. ሕጉን መጠበቅ – መዝ. 119:33፤34፤145
3. ሐሳቡን መጠበቅ – መዝ. 119:56፤69፤100
4. ትእዛዛቱን መጠበቅ – መዝ. 119:115
5. ሕጉን መጠበቅ – መዝ. 119:34

▣ **"በፍጹም ልባቸው"** አጠቃላይ መሰጠት ዋነኛ ነገር ነው (ዘዳ. 4:29፤6:5፤10:12፤11:13፤13:3፤30:2)። ይህ ፈሊጥ ሆኗል፣ ለያህዌና ለፍቃዱ አጠቃላይ መሰጠት። ዳዊት እንደዚህ ዓይነት ልብ ነበረው፣ ሰሎሞንም እንደ ነበረው ሁሉ፣ የእርጅና ዘመኑ እስኪደርስ! መሰጠት አንድ ነጥብ ላይ፣ በአንዱ ሕይወት በቂ አይሆንም! ዳዊት ኃጢአትን ሠራ ነገር ግን ንስሐ ገባ። ግንኙነትን ማደስ ቁልፍ ነገር ነው፣ ኃጢአት-የለሽነት ሳይሆን (1 ዮሐንስ 1፡9)።

**119፡6 "አላፍርም"** በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) "እፍረት" ሁለቱም አለው

1. ውስጣዊ ገጽታ — የእፍረት ስሜት በሕዝብ ፊት በመዋረድ፣ የመናቅ ስሜት በቤተሰብ እና ባልንጀሮች፣ የስም መጥፋት
2. ውጫዊ ገጽታ — ደሀ መሆን፣ አቅመ-ቢስ
3. ሃይማኖታዊ ገጽታ — በያህዌ መናቅ፣ መዝ. 25:20፤31:1፤71:1፤119:6፣31፣46፣80

መዝሙራት ዘወትር እግዚአብሔርን ይጠይቃሉ፣ ጠላቶችን "እንዲያሳፍር" (መዝ. 35:4፤70:2፤71:13፤86:17፤119:78፤ደግሞም ማቴ. 10:33፤ማርቆስ 8:38፤ሉቃስ 12:9) ተመልከት።

**119:8 "በፍጹም አትጣለኝ"** ይህ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 736፣ ኬቢ. 806፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ነው ጥቅም ላይ የዋለ) ወደ ያህዌ የሚደረግ ተደጋጋሚ ጩኸት ነው (መዝ. 38:21፤71:9፣18)። አትራቅ፣ ወይም ከገዛ ራሴ አቅም ጋር አትተወኝ!

## መዝሙር ፡119፡1-8 (ቤት)

**[9]ጕልማሳ መንገዱን በምን ያነጻል?**
**ቃልህን በመጠበቅ ነው።**

[10]**በፍጹም ልቤ ፈለግሁህ፥**
**ከትእዛዝህ አታርቀኝ።**
[11]**አንተ እንዳልበድል፥**
**ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።**
[12]**አቤቱ፥ አንተ ቡሩክ ነህ**
**ሥርዓትህን አስተምረኝ።**
[13]**የአፍህን ፍርድ ሁሉ**
**በከንፈሬ ነገርሁ።**
[14]**እንደ ብልጥግና ሁሉ**
**በምስክርህ መንገድ ደስ አለኝ።**
[15]**ትእዛዝህን አሰላስላለሁ፥**
**መንገድህንም እፈልጋለሁ።**
[16]**በትእዛዝህ ደስ ይለኛል**
**ቃልህንም አልረሳም።**

**119፡9 "ጎልማሳ"** የመዝሙር 119 ጸሐፊ "ለወጣት" ተከታዮች አዘውትሮ ይገልጻል፣ መልካም አኗኗራቸውን አጠንክረው እንዲይዙ።

ንጹሕ መንገድ ተገልጿል፣ የእግዚአብሔርን ራዕይ መጠበቅ እንደሆነ (ማለትም፣ ቃል)። ይኸው ቋሚ የሆነ "ጥበቃን" እንደሚሻ ተገልጿል (ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581)።

**119፡10 "በፍጹም ልቤ"** መዝ. 119፡2ለ ላይ ማስታወሻ ተመልከት።

▣ **"ፈለግሁህ"** ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ 205፣ ኬቢ 233) ተደጋግሞ ጥቅም ላይ ውሏል፣ በዚህ መዝሙር ላይ (መዝ. 119:2፤10፤45፣ 94፤155)። እሱም የሚገልጸው የጸሎትን፣ የጥናትን፣ እና የአምልኮን የጸና ሕይወት ነው።

▣ **"ዞር ማለት"** ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ 993፣ ኬቢ 1413፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ) በአሉታዊ ዓረፍተ ነገር ይገኛል፣ መዝ. 119:21፤118 ላይ። እሱም ሦስት ጊዜ ብቻ መዝሙር ላይ ይገኛል፣ ነገር ግን ስድስት ጊዜ ምሳሌ ላይ። እሱም ጥቅም ላይ የዋለው "ሆን ተብሎ ላልተደረገ ኃጢአት ነው" ሌዋ. 4:13፤ዘኍ. 15:22 ላይ። "ከዛ" መጠንቀቅ ይገባል፣ ታማኝ ተከታዮች ዓይናቸውን እንዳያነሡ፣ በግልጽ ከተቀመጠው የያህዌ መንገድ።

**119፡11 "ቃልህን በልቤ ሰወርሁ።"** ይህ የሐረግ ምሥረታ ማርያም ለመልአኩ በሰጠችው ምላሽ ጥቅም ላይ ውሏል (ሉቃስ 2፡19፤51)። የእግዚአብሔር ቃል እጅግ ዋጋ ያለው ነው (መዝሙር 19:10፤119:14ለ)። መጽሐፍ ቅዱስህ ለአንተ እጅግ ዋጋ አለውን? ታነበዋለህን፣ ታጠናዋለህን፣ ታደርገዋለህን፣ ብሎም ለሌሎች ታስተምረዋለህን (ዕዝራ 7፡10)?

ይህ *ግሥ* (ቢዲቢ 860፣ ኬቢ 1049፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) በጥሬው "መደበቅ" ማለት ነው፣ እናም ፈሊጥ ነው፣ የእግዚአብሔርን ቃል ለማስታወስ (ኢዮብ 23:12፤ምሳ. 2:1፤7:1)።

**119:12 "አስተምረኝ"** ይህ *ፒል* ተተኳሪ ነው (ቢዲቢ 540፣ ኬቢ 531)። እሱም በመዝሙር 119 ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል (ዝከ. 119:7፤12፤26፤ 64፤66፤68፤71፤73፤99፤108፤124፤135፤171)። እውነት በሰዎች ጥረት አይመጣም፣ ነገር ግን በ

1. በእግዚአብሔር መንፈስ
2. በእግዚአብሔር ራዕይ
3. ለእግዚአብሔር በሆነ የግል መሰጠት
4. በጽኑ ጥናት
5. በግል ትግበራ

**119፡13** ይህ የቅኔ ሐረግ በመቅደስ የአምልኮ መቼትን ያመለክታል።

**119፡14** ለታማኝ ተከታይ የእግዚአብሔር ራዕይ በምድር ላይ እጅግ ዋጋ ያለው ነገር ነው (መዝ. 19:10፤ 119:72፤127፤ምሳ. 8:10፤11፤19)።

**119:15** ይህ ቁጥር ሁለት ተጓዳኞች አሉት።

1. ማሰላሰል – ቢዲቢ 967፣ ኬቢ 1319፣ *ቃል*፣ መዝ. 119:23፤27፤48 (ሁለቴ)፣ 78፤148። የእግዚአብሔርን ቃል በማሰላሰል ነው የመዝሙር መጽሐፍ የሚጀምረው (መዝ. 1:2)። ይህ ማሰላሰል ዘዳ. 6:6-9 ላይ ተመልክቷል።
2. መመልከት– ቢዲቢ 613፣ ኬቢ 661፣ *ሂፊል*፣ መዝ. 119:6፤15፤18

እነዚህ ሁለቱ ጽኑ ጥናትን ያመለክታሉ! ይህ ጊዜ፣ ጥረት፣ ቁርጠኝነት፣ እና መርሐ-ግብር ይጠይቃል! የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጓሜ ሴሚናር www.freebiblecommentary.org ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ላይ ተመልከት።

**119:16 "ደስ ይለኛል"** ቢዲቢ 1044፣ ኬቢ 1613፣ *ሂዝፓል* ያልተጠናቀቀ፣ መዝ. 19:24፤35፤47፤70፤77፣ 92፤143፤174።

▣ **"አልረሳም"** ቢዲቢ 1013፣ ኬቢ 1489፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ በአሉታዊ፣ መዝ. 119:61፤83፤93፤109፤141፣ 153፤176 (የመዝሙር 119 የመጨረሻው ስንኝ)።

**መዝሙር ፡119፡17-24 (ጋሜል)**

[17]**ለባሪያህ መልካም አድርግ**
**ሕያው እንድሆን፥ ቃልህንም እንድጠብቅ።**
[18]**ዓይኖቼን ክፈት፥**
**ከሕግህም ተኣምራትህን አያለሁ።**
[19]**እኔ በምድር እንግዳ ነኝ**
**ትእዛዛትህን ከእኔ አትሰውር።**
[20]**ነፍሴ ሁልጊዜ ፍርድህን**
**እጅግ ናፈቀች።**
[21]**ከትእዛዛትህ የሳቱትን**
**ትዕቢተኞችንና ርጉማንን ዘለፍህ።**
[22]**ምስክርህን ፈልጌአለሁና።**
**ስድብንና ነውርን ከእኔ አርቅ።**
[23]**አለቆች ደግሞ ተቀምጠው እኔን አሙኝ**
**ባሪያህ ግን ሕግህን ያሰላስል ነበር።**
[24]**ምስክርህም ተድላዬ ነው፥**
***ሥርዓትህም መካሪዬ ነው።***

**119፡17** *መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ባርኮት እየለመነ እንደሆነ ተገንዘብ (ማለትም፣ "መልካም አድርግ"* ቢ.ዲ.ቢ 168፣ ኬ.ቢ 197፣ *ቃል ተተኳሪ*) የተሻለ "ባርያ" ይሆን ዘንድ እንዲረዳው (ቢ.ዲ.ቢ 713)።

1. ሕያው እንድሆን – ቢ.ዲ.ቢ 310፣ ኬ.ቢ 309፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ* መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ቃልህን እጠብቅ ዘንድ – ቢ.ዲ.ቢ 1036፣ ኬ.ቢ 1581፣ *ቃል ተጓዳኝ*

ባርኮቶቹ ለግላዊ ጠቀሜታ ወይም ምቾት አይደሉም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን *ሥራ* በምድር ላይ ለማጠንከር፣ ጥልቅ ለማድረግ፣ እና ለማተለቅ እንጂ።

▣ ***"ቃልህ"*** *መዝ.* 119፡1 ላይ ማስታወሻ ተመልከት፣ እንዲሁም ልዩ ርዕስ፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ።

**119፡18** *ተመሳሳይ ርዕዮተ-ዓለም፣ እግዚአብሔር አገልጋዮቹን የሚያስታጥቀው እዚህ ቁጥር ላይ ተገልጿል። ማንም መመልከት ("መግለጥ፣" ቢ.ዲ.ቢ* 162፣ ኬ.ቢ 161፣ *ፒል ተተኳሪ*) ወይም የእግዚአብሔርን ፍቃድና መንገዶቹን መረዳት አይችልም፣ ካለ እርሱ ዕርዳታ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማብራራት (ማብራት)።

▣ ***"ተአምራት"*** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተአምራት።

▣ ***"ሕግህ"*** *ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ.* 119፡1 ላይ።

**119፡19 "እኔ በምድር እንግዳ ነኝ"** ይህ የታማኝ ተከታይ ርዕዮተ-ዓለም ነው። የዘፍጥረት 3 ውድቀት ይሄንን ዓለም ወደ እንግድነትና ምነና ቀየረው (1 ዜና. 29፡15፤መዝ. 119፡54፤ዕብራውያን 11፡13-16)። ከፈጣሪያችን ጋር ጥልቅ የሆነ ኅብረት እንዲኖረን እንናፍቃለን፣ ወደ ተፈጠርንበት ኅብረት (ዘፍ. 1፡26፤27፤3፡8)። ይህ ዓለም ከእንግዲህ ቤታችን አይደለም!

"እንግዳ/መጻተኛ" የሚለው ዘይቤ (ቢ.ዲ.ቢ 158) የመጣው ያህዌ ለአብርሃም ከተናገረው ቃል ነው፣ ዘርዮቹ በግብፅ በእንግድነት እንደሚኖሩ (ዘፍ. 15፡13)። አብርሃም ራሱን በዚህ ቃል ጠርቷል፣ ዘፍ. 23፡4 ላይ። እሱም ከሙሴ ልጆች ለአንደኛው ስም ሆኗል፣ ዘጸ. 2፡22። እስራኤላውያን ተነግሯቸዋል፣ ፍትሕና ምሕረትን "ለእንግዶች/መጻተኞች" እንዲሰጡ፣ ምክንያቱም እነርሱም በአንድ ወቅት እንዲያ ስለነበሩ (ዘጸ. 23፡9)። አብርሃም የእግዚአብሔርን ከተማ እንደሚፈልግ ተብሎለት ነበር (ዕብ. 11፡10)። ይህም ከዚህ ሕይወት ዳርቻ በላይ ነው። እግዚአብሔር ዘላለማዊነትን ከታማኝ ተከታዮቹ ጋር መካፈል ይፈልጋል!

▣ **"ትእዛዛትህን ከእኔ አትሰውር።"** *ኃጢአት መንፈሳዊ ዕውርነትን አምጥቷል* (1 ቆሮ. 13፡12)። *መጽሐፍ ቅዱስ ለሁለት ዓይነት መንፈሳዊ ዕውርነት እውቅና ይሰጣል።*

1. *አምላክ ያመጣው* (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር ያደነደነው)
2. በራስ የመጣ (ማለትም፣ ዮሐንስ 9፡13-41)

**119፡20** እውነተኛ *ታማኝ* ተከታይ እግዚአብሔርንና ቃሉን ይሻል፣ በአንድ ልብ ጽናት!

*"መድቀቅ"* የሚለው *ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ 176፣ ኬ.ቢ 203፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) እዚህጋ ብቻ እና ሰቆ. 3፡16 ላይ ነው የሚገኘው። *"መናፈቅ"* (ቢ.ዲ.ቢ 1060) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው።

▣ **"ነፍስ"** "ነፍስ" ያህዌን ትናፍቃለች (መዝ. 42፡2፤63፡2፤119፡81፤143፡6)። ስለ *ኔፊሽ ማብራሪያ* (ቢ.ዲ.ቢ 659) ማስታወሻ ተመልከት ዘፍ. 35፡18 www.freebiblecommentary.org ላይ፣ ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር።

**119፡21** እምነተ-ቢሶች ባሕርያቸው

1. ትዕቢተኛ (ማለትም፣ ያወቁ ነገር ግን ዓመጻን የመረጡ) – ቢ.ዲ.ቢ 267፣ መዝ. 86፡14፤119፡51፤69፤78፤85፤122

2. የተረገሙ – ቢዲቢ 76፣ ኬቢ 91
3. ከእግዚአብሔር ትእዛዝ ዞር የሚሉ – ቢዲቢ 993፣ ኬቢ 1413

**119:22 "ስድብንና ነውርን ከእኔ አርቅ።"** *ግሡ* ("አንከባል፣" ቢዲቢ 164፣ ኬቢ 193፣ *ቃል ተተኳሪ*) የይቅርታ ጸሎት ነው።
1. ስድብ – ቢዲቢ 357፣ *መዝ*. 69:19፣20
2. ነውር – ቢዲቢ 100 II፣ *መዝ*. 123:3-4

እግዚአብሔር ይቅር የሚልበት ምክንያት፣ መዝሙረኛው ትእዛዙን ስላስተዋለ ነው (ማለትም፣ ሁለቱ መንገዶች፣ ዘዳ. 30፡15፣19)። በሊቃውንት መካከል አንዳንድ ውይይት ተካሂዷል፣ ከየትኛው የዕብራይስጥ ሥር የመዝ. 119፡22ሀ ግሥ እንደ መጣ።
1. ገለጥ – ("ጉልህ ማድረግ፣" ገ̃ለ ፣ ቢዲቢ 164 [ኤምቲ])
2. ማንከባለል – ጎ̃ለ ፣ ቢዲቢ 164 II ከኢያ. 5:9፣መዝ. 22:9

**119:23-24 "አለቆች ደግሞ ተቀምጠው እኔን አሙኝ"** "አለቆች" የሚለው አጠቃቀም (ቢዲቢ 978፣ *መዝ*. 118:9) አንድምታው
1. መዝሙረኛው ባለጠጋ፣ ብርቱ መሪ፣ ንጉሥ ሊሆን የሚችል ነው
2. በብሔረ-አመራሩ ውስጥ ውጥረት አለ

ምንም እንኳ ሁከትና ነውጥ ቢሆንም መዝሙረኛው በእግዚአብሔር ራዕይ እውነትና ተስፋ ላይ አተኩሯል። እውነተኛ ሰላምና መረጋጋት ሊገኝ የሚችለው እሱጋ ብቻ ነው፣ ሁኔታዎች ሳይሆኑ ወይም በቶሎ የሚያልፍ ዝና፣ ሥልጣን፣ ወይም ማዕርግ።

ፔሺታ "አለቆች"ን የሚተረጉመው (ቢዲቢ 978፣ መዝ. 119:161) "መልካም ያልሆኑ"ወይም "ክፉ ሰዎች" በሚል ነው፣ ይኸውም ማንኛውንም ፍንጭ የሚያስወግድ፣ መዝሙረኛው እንደ መሪ ያለውን ሥልጣን።

**መዝሙር ፡119፡25-32 (ዳሌጥ)**

[25]ነፍሴ ወደ ምድር ተጣጋች
እንደ ቃልህ ሕያው አድርገኝ።
[26]መንገድህን ነገርሁ ሰማኸኝም
ሥርዓትህን አስተምረኝ።
[27]የሥርዓትህን መንገድ እንዳስተውል አድርገኝ፥
ተኣምራትህንም አሰላስላለሁ።
[28]ከኀዘን የተነሣ ነፍሴ አንቀላፋች
በቃልህ አጠንክረኝ።
[29]የዓመፅን መንገድ ከእኔ አርቅ፥
በሕግህም ማረኝ
[30]የእውነትህን መንገድ መረጥሁ፥
ፍርድህንም አልረሳሁም።
[31]አቤቱ፥ ምስክርህን ተጠጋሁ
አታሳፍረኝ።
[32]ልቤን ባሰፋኸው ጊዜ፥
በትእዛዝህ መንገድ ሮጥሁ።

**119፡25** የመጀመሪያው ስንኝ መዝሙረኛው ያለበትን መቼት ያሳያል (መዝ. 44፡25)። እሱ ወደ ሞት የተቃረበ መስሎታል፣ በሕመም ይሁን በዓመጻ አልታወቀም፣ ነገር ግን መዝ. 119፡23 የቤተ-መንግሥት ሴራ እንደሆነ ያመለክታል (ምንም እንኳ ከመዝሙሩ መስቀልያ ባሕርይ አወቃቀር የተነሣ፣ ርግጠኝነት ባይኖረውም፣ ጽሑፋዊ ዐውዱ ወይም ዜማው መሪ ይዘቱ ለመሆኑ)።

መዝሙረኛው ተከታታይ የጸሎት ጥያቄዎች አሉት።
1. እንደ ቃልህ ሕያው አድርገኝ፣ መዝ. 119:25ለ – ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ *ፒል ተተኳሪ*፣ መዝ. 119:37፣40፣88፣93፣107፣149፣154፣156፣159። ማለት የሚሆነው
   ሀ. ጠብቀኝ
   ለ. አድሰኝ
2. ሥርዓትህን አስተምረኝ መዝ. 119:26ለ – ቢዲቢ 540፣ ኬቢ 531፣ *ፒል ተተኳሪ*፣ ዝኪ. 119:12፣26፣64፣68፣ 108፣124፣135፣171
3. የሥርዓትህን መንገድ እንዳስተውል አድርገኝ መዝ. 119:27ሀ – ቢዲቢ 106፣ ኬቢ 122፣ *ሂፊል ተተኳሪ*፣ ዝኪ. 119:34፣73፣125፣144፣169
4. በቃልህ አጠንክረኝ፣ መዝ. 119:28ለ – ቢዲቢ 827፣ ኬቢ 1086፣ *ፔል ተተኳሪ*። ቢዲቢ የሚለው የፔል ግሡ ፍቺ
   ሀ. ፈጽም፣ መዝ. 119፡106
   ለ. አጽና፣ እዚህጋ
5. የሐሰትን መንገድ ከእኔ አርቅ፣ መዝ. 119:29ሀ – ቢዲቢ 693፣ ኬቢ 747፣ *ሂፊልተተኳሪ*። "የሐሰት መንገድ" የ "ዘላለም መንገድ" ቀጥተኛ ተቃራኒ ነው፣ የመዝ. 139፡24።
6. በሕግህም ማረኝ፣ መዝ. 119:29ለ – ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ የእግዚአብሔር ራዕይ "የታመነ መንገድ" ነው (መዝ. 119:30)።

**119:30-32** መዝሙረኛው የሚያደርጋቸውን፣ ያደረጋቸውን ብዙ ነገሮች ተገንዘብ፣ እግዚአብሔር በራዕዩ በኩል በሰጠው መረዳት።
1. እሱ ጸልዮአል (*ፒል* የተጠናቀቀ)፣ መዝ. 119:26ሀ
2. እሱ መርጧል (*ቃል* የተጠናቀቀ) የታመነውን መንገድ መዝ. 119:30ሀ

3. እሱ አኑሯል (ፒል የተጠናቀቀ) የእግዚአብሔርን ራዕይ በፊት ለፊቱ ("የእግዚአብሔር ሥርዓት ረብ እንዳለው ቆጥሯል")፣ መዝ. 119:30ለ
4. እሱ ተጣብቋል (ቃል የተጠናቀቀ፣ cf. 119:25 ከእግዚአብሔር ራዕይ ጋር፣ መዝ. 119:31ሀ (ዘዳ. 10:20 ላይ እሱ ጥቅም ላይ የዋለው ከእግዚአብሔር ጋር ለመጣበቅ ነው፤ በዚህ መዝሙር ላይ የእግዚአብሔር ሰውና ራዕይ ተዋህደዋል)
5. ይሮጣል (ቃል ያልተጠናቀቀ) በእግዚአብሔት ራዕይ መንገድ፣ መዝ. 119:32ሀ

**119:32ለ "ልቤን ባሰፋኸው ጊዜ፥"** እግዚአብሔር ይጨምራል ( "ያሳድጋል፣" ቢዲቢ 931፣ ኬቢ 1210፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ) የመዝሙረኛውን አቅም፣ የእግዚአብሔርን እውቀት በመረዳትና በድርጊት።

ለ "ልብ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ።

**መዝሙር ፡119፡33-40 (ሄ)**

**33አቤቱ፥ የሥርዓትህን መንገድ አስተምረኝ፥**
**ሁልጊዜም እፈልገዋለሁ።**
**34እንዳስተውል አድርገኝ፥ ሕግህንም እፈልጋለሁ**
**በፍጹም ልቤም እጠብቀዋለሁ።**
**35እርስዋን ወድጃለሁና**
**የትእዛዝህን መንገድ ምራኝ።**
**36ልቤን ወደ ምስክርህ አዘንብል፥**
**ወደ ስስትም አይሁን።**
**37ከንቱ ነገርን እንዳያዩ ዓይኖቼን መልስ**
**በመንገድህ ሕያው አድርገኝ።**
**38እንዲፈራህ**
**ባሪያህን በቃልህ አጽና።**
**39ፍርድህ መልካም ናትና**
**የተጠራጠርሁትን ስድብ ከእኔ አርቅ።**
**40እነሆ፥ ትእዛዝህን ናፈቅሁ**
**በጽድቅህ ሕያው አድርገኝ**

**119፡33-40** ይህ አንጓ ልመናን ባሕርይ ያደረገ ነው (9 ተተኳሪዎች) እግዚአብሔር መዝሙረኛውን እንዲያስተምረውና እንዲያስችለው፣ እነዚያን ትእዛዛት እንዲኖር። ይህም ሹማ ከሚለው ግሥ ጋር ተመሳሳይ ነው (ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570)፣ ፍችውም "ማድመጥ ለመስማት" የሆነ። የእግዚአብሔር ራዕይ ከሕግጋትና ከደንብ በላይ ነው፣ እሱም መልካም አኗኗር ነው!

"መንገድ" የሚለው ቃል መዝሙራት ላይ ተዘውትሮ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እሱም ይሄንን የሕይወት ስልት፣ በየቀኑ፣ የፍቃደኝነት መታዘዝን ይገልጻል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ። እንዴት እንደሆነ ተገንዘብ፡

1. አስተምረኝ – እፈልገዋለሁ፣ መዝ. 119:33
2. ማስተዋልን ስጠኝ – እንዳስተውለው፣ መዝ. 119:34

**119፡35** ለታማኝ ተከታይ፣ መታዘዝ አሰልቺ ወይም ሕጋዊ አይደለም፣ ደስታ እንጂ።

**119፡36-39** መዝሙረኛው ሁለት ነገሮችን ይጠቅሳል፣ የሚፈራቸውን፣ ልቡን ከእግዚአብሔር ሊወስዱ የሚችሉትን።

1. ታማኝነት የሌለበት ጠቀሜታ፣ መዝ. 119:36ለ
2. ከንቱነትን የሚመለከቱ ዓይኖች፣ መዝ. 119:37ሀ

እሱም መንፈሳዊ ነገሮችን ያለ እግዚአብሔር ርዳታ መቀዳጀት እንደማይችል ተረድቷል።

1. አስተምረኝ፣ መዝ. 119:33 – ቢዲቢ 434፣ ኬቢ 436፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ መዝ. 25:4፤27:11፤86:11
2. ማስተዋልን ስጠኝ፣ መዝ. 119:34 – ቢዲቢ 106፣ ኬቢ 122፣ ሂፊል ተተኳሪ
3. በመንገድህ እንድራመድ አድርገኝ መዝ. 119:35 – ቢዲቢ 201፣ ኬቢ 231፣ ሂፊል ተተኳሪ
4. ልቤን አዘንብል፣ መዝ. 119:36 – ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ ሂፊል ተተኳሪ
5. ዓይኖቼን መልስ፣ መዝ. 119:37ሀ – ቢዲቢ 716፣ ኬቢ 778፣ ሂፊል ተተኳሪ
6. አድሰኝ፣ መዝ. 119:37ለ – ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ ፒል ተተኳሪ
7. ቃልህን በውስጤ አጽና፣ መዝ. 119:38 – ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ ሂፊል ተተኳሪ

ግን ደግሞ መለኮታዊ ድርጊቶችን (ሂፊል ተተኳሪ) መቀዳጀት የሚቻለው በመልካም ምርጫ እና ውሳኔዎች እንደሆነ ተገንዘብ (ተከታታይ ተጓዳኞች እና የተጠናቀቁዎች ለሰዎች ድርጊቶች ጥቅም ላይ ውለዋል)።

1. እመለከታለሁ፣ መዝ. 119:33ለ – ቢዲቢ 665፣ ኬቢ 718፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. እመለከት ዘንድ፣ መዝ. 119:34ሀ – እንደ ቁ. 1 ግን ቃል ተጓዳኝ
3. እጠብቃለሁ፣ መዝ. 119:34ለ – ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
4. ደስ ይለኛል፣ መዝ. 119:35ለ – ቢዲቢ 342፣ ኬቢ 339፣ ቃል የተጠናቀቀ
5. ሐሳብህን እናፍቃለሁ፣ መዝ. 119:40ሀ – ቢዲቢ 1060፣ ኬቢ 1672፣ ቃል የተጠናቀቀ

ሚዛኑን ታያላችሁን? ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምርጫ/ዕጣ ፈንታ እና የሥነ-መለኮታዊ ሚዛን አስፈላጊነት እና ልዩ ርዕስ፡ ዕጣ ፈንታ(ካልቪኒዝም) አልያም የሰው ነጻ ፍቃድ (አርሚኒያኒዝም)።

**119:34 “በፍጹም ልቤ”** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 119:2 ላይ።

**119:37 “ከንቱነት”** ይህ ጣዖት አምላኪነትን ሊያመለክት ይችላል (መዝ. 24:4፤101:3)። መዝሙር 119:48 የሚጠቅሰው “የማንሣት መዝሙራትን” ነው (ማለትም፣ “እጆቼን አነሣለሁ”)፣ እሱም መዝ. 44:20-21 ላይ ለጣዖት አምልኮ ጥቅም ላይ የዋለ።

▣ **“አድስ”** ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (መዝ. 119:25፣37፣40፣88፣93፣107፣149፣154፣156፣159)። ግሡ (“መኖር፣” ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ ፒል ተተኳሪ ሰፊ የፍች መስክ አለው) “በሕይወት መኖር” ነው። “እውነተኛው” ብቸኛ ሕይወት ከያህዌ ጋር ያለ ኅብረት ነው፣ ከሕይወት ሰጭው ጋር። እውነተኛ ሕይወት ሁለት ይዘቶች አሉት።

1. ሥጋዊ ሕይወት
2. መንፈሳዊ ሕይወት

**119:38 “አንተን መፍራት በውስጤ እንዲፈጠር”** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፍርሃት (ብኪ)።

**119:39 “ፍርድህ መልካም ናትና”** እንደገና ለእግዚአብሔር ራዕይ የተጠቀሱት አስተዋጽዖዎች ደግሞ ለእግዚአብሔር ለራሱ መጠቀሳቸውን (1 ዜና. 16:34፤መዝ. 25:8፤34:8፤73:1፤86:5፤100:5፤106:1፤107:1፤118:1፣29፤119:68፤135:3፤136:1፤145:9፤ኤር. 33:11)። እዚህ “መልካም” የሚለው ቅጽል ነው (ቢዲቢ 373 II)።

ይህ መዝሙር ስለ እግዚአብሔር ራዕይ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን ስለ እግዚአብሔር ስለ ራሱ እንጂ!

**119:40 “ጽድቅ”** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ።

## መዝሙር :119:41-48 (ዋው)

**41 አቤቱ፥ እንደ ቃልህ፥**
**ምሕረትህና መድኃኒትህ ይምጡልኝ።**
**42 በቃልህ ታምኛለሁና**
**ለሚሰድቡኝ በነገር እመልስላቸዋለሁ።**
**43 በፍርድህም ታምኛለሁና**
**የእውነትን ቃል ከአፌ ፈጽመህ አታርቅ።**
**44 ለዘላለም ዓለም**
**ሁልጊዜ ሕግህን እጠብቃለሁ።**
**45 ትእዛዛትህንም ፈልጌአለሁና**
**አስፍቼ እሄዳለሁ።**
**46 በነገሥታት ፊት ምስክርህን እናገራለሁ፥**
**አላፍርምም**
**47 እጅግም በወደድኋቸው**
**በትእዛዛትህ ደስ ይለኛል።**
**48 እጆቼንም ወደ ወደድኋቸው**
**ወደ ትእዛዛትህ አነሣለሁ**
**ሥርዓትህንም አሰላስላሁ**

**119:41-48** ይህ አንዳ ባሕርይ ያደረገው ተጓዳኞችንና ነጠላ ግሦችን ነው።

1. ምላሽ ይኖረኛል፣ መዝ. 119:42ሀ – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. እና እታመናለሁ፣ መዝ. 119:42ለ – ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ነጠላ
3. እኔ እጠብቃለሁ መዝ. 119:43ለ – ቢዲቢ 403፣ ኬቢ 407፣ *ፒል* የተጠናቀቀ፣ ነጠላ
4. እኔ እጠብቃለሁ፣ መዝ. 119:44ሀ – ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ *ቃል* ተጓዳኝ፣ ነጠላ
5. እራመዳለሁ፣ መዝ. 119:45ሀ – ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ *ሂዝፓል* ተጓዳኝ፣ ነጠላ
6. እሻለሁ፣ መዝ. 119:45ለ – ቢዲቢ 205፣ ኬቢ 233፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ነጠላ
7. እናገራለሁ፣ መዝ. 119:46ሀ – ቢዲቢ 180፣ ኬቢ 210፣ *ፒል* ተጓዳኝ፣ ነጠላ
8. ደስ ይለኛል፣ መዝ. 119:47ሀ – ቢዲቢ 1044፣ ኬቢ 1613፣ *ሂዝፓልፔል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
9. እወዳለሁ፣ መዝ. 119:47ለ – ቢዲቢ 12፣ ኬቢ 17፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ ነጠላ
10. አነሣለሁ፣ መዝ. 119:48ሀ – ቢዲቢ 669፣ ኬቢ 724፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ ነጠላ፣ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
11. እወዳለሁ፣ መዝ. 119:48ለ – እንደ ቁ. 9
12. አሰላስላለሁ፣ መዝ. 119:48ሐ – ቢዲቢ 967፣ ኬቢ 1319፣ *ቃል* ተጓዳኝ፣ ነጠላ

እግዚአብሔርንና የእርሱን ራዕይ ማወቅ የግል ምላሽን ይጠይቃል!

**119:41** “ምሕረት” (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት [ሄሰድ]) እና “ደኅንነት” (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት [ብኪ]) ሰውኛ ዘይቤ መደረጋቸውን ተገንዝብ፣ ወደ ታማኝ ተከታዮች እንደሚመጡ ነገሮች። በዚህ ምክንያት እነርሱ በመልካም መንገድ ነው የሚያደርጉት።

**119:43ሀ** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል ተጽዕኗዊ*) ፍችው “ነጥቆ መውሰድ” ነው። እሱም ጥቅም ላይ የሚውለው ለመታደግ ነው

1. ከሞት – ዘዳ. 32:39፤መዝ. 22:20፤33:19፤56:14፤86:13፤ምሳ. 24:11

2. ከኃጢአት – መዝ. 39፡9፤79፡9

እዚህጋ የሚዛመደው ከመዝ. 119:42 ጋር ነው፣ ይኸውም ከእግዚአብሔር ራዕይ መልስ መገኘቱን የሚገልጽ፣ በመዝሙረኛው ላይ ለሚሳለቁበት (የተሻለ የአኪ ማሳያ ማቴ. 10:19-22፤ማርቆስ 13:9-12፣ በተለይም፣ ማርቆስ 13:11፤ሉቃስ 21:12-19)።

**119፡44** ይህ የቅኔ ስንኝ አጽንዖት የሚሰጠው የወቅቱንና የወደፊቱን የእግዚአብሔር ራዕይ ጠቀሜታ ነው (ማቴ. 5፡17-19)።

**119፡46** ይህ የሚገልጸው የታማኝ ተከታዮችን

1. ምስክርነት ለተሸነፉ ነገሥታት
2. ከባዕድ ሕዝቦች ጋር ቃል ኪዳን የመጋባትን ገጽታ
3. ለብርቱ ወይም ለተማሩ ሰዎች ዘይቤ ነው

**119፡48ሀ** "እጆችን ማንሣት" በእስራኤል ባህል ሁነኛው አቋም ነበር፣ ለጸሎት (መዝ. 28:2፤63:4፤134:2፤
141:2፤143:6፤ሰቆ. 2:19፤1 ጢሞ. 2:8)። እንደገና፣ አንዱ ዘወትር "እጆቹን የሚያነሣው" ለእግዚአብሔር ለራሱ ነበር፣ ነገር ግን እዚህጋ ለራሱ (ለእግዚአብሔር) ራዕይ ነው።

▣ **"አሰላስላለሁ"** ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 119፡15 ላይ።

## መዝሙር ፡119፡49-56 (ዛይ)

**49ለባሪያህ ተስፋ ያስደረግኸውን**
**ቃልህን አስብ።**
**50ቃልህ ሕያው አድርጎኛልና**
**ይህች በመከራዬ ደስ አሰኘችኝ።**
**51ትዕቢተኞች እጅግ ዐመፁ**
**እኔ ግን ከሕግህ አልራቅሁም።**
**52ከጥንት የነበረውን ፍርድህን አሰብሁ፥ አቤቱ፥**
**ተጽናናሁም።**
**53ሕግህን ከተዉ**
**ከኃጢአተኞች የተነሣ ኀዘን ያዘኝ።**
**54በእንግድነቴ አገር**
**ሥርዓትህ መዝሙር ሆነችኝ።**
**55አቤቱ፥ በሌሊት ስምህን አሰብሁ፥**
**ሕግህንም ጠበቅሁ።**
**56ትእዛዛትህንም ፈልጌአለሁና**
**ይህች ሆነችልኝ።**

**119፡49 "አስብ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 269፣ ኬቢ 269) ሦስት ጊዜ በዚህ አንጓ ላይ ይከሰታል።

1. መዝ. 119:49 – *ቃል ተተኳሪ*
2. መዝ. 119:52 – *ቃል የተጠናቀቀ*
3. መዝ. 119:55 – *ቃል የተጠናቀቀ*

መዝሙረኛው ያህዌን ይለምናል እንዲያስበው (119:49) እሱ ስላሰበውና ስለ ታዘዘው (መዝ. 119:55ለ፤56ለ)።

ሁሉም ግሦች (ከመጀመሪያው ተተኳሪ በቀር) የተጠናቀቁ ወይም ያልተጠናቀቁ መሆናቸውን ተገንዘብ፣ ከዋው ጋር (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የዕብራይስጥ ሰዋሰው)። የመዝሙረኛው እውቀትና ድርጊት የተረጋጋ ርዕዮተ-ዓለም፣ የሕይወት ስልት እውነታዎች ናቸው! የእግዚአብሔር ቃል መረጃ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን

1. ተስፋ፣ መዝ. 119:49ለ
2. መጽናኛ፣ መዝ. 119:50ሀ፣ 52ለ
3. ጽናት፣ መዝ. 119:50ለ
4. የሕይወት መመሪያ፣ መዝ. 119:51ለ
5. ዝማሬ፣ መዝ. 119:54ሀ
6. በሌሊት ሐሳብ፣ መዝ. 119:55ሀ
7. መዝ. 119:56ሀ
   ሀ. ደስታ – አእቅ
   ለ. ባርኮት – አየተመቅ
   ሐ. መጽናኛ – ፔሺታ

▣ **"ባርያህ"** እዚህ እሱ የሚያመለክተው፣ ታማኝ ተከታይን ነው፣ እሱም የእግዚአብሔርን ቃል የሚሻ፣ የሚያውቅ፣ እና ተስፋ የሚያደርግ። ማስታወሻ ተመልከት ዘዳ. 34:5 ላይ ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር www.freebiblecommentary.org. ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ባሪያዬ።

▣ **"ተስፋ"** ይህ በጥሬው "መጠበቅ" ማለት ነው (ቢዲቢ 430፣ ኬቢ 407፣ ፒል የተጠናቀቀ)። የእግዚአብሔር ተስፋዎች እስኪፈጸሙ ድረስ መጠበቅ የሁለቱም የእምነትና ተስፋ ድርጊት ሐሳብ ነው። ምናልባት፣ ሊሆን ይችላል በሚል ተስፋ ማድረግ አይደለም፣ ነገር ግን - በርግጠኝነት -

ገና ርግጠኛ - ያልሆኑትን - በጊዜ ውስጥ- ተስፋ ማድረግ ነው (ከአኪ አጠቃቀም ጋር ይመሳሰላል፣ ከዳግም ምጽአቱ ጋር በተያያዘ)። እሱም መዝሙር ላይ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (መዝ. 31:24፤33:18፣22፤71:4፤119:49፣74፣81፣114፣147፤በተጠቃለለ መልኩ መዝ. 130:7፤131:3)። ይህ ሐሳብ ሮሜ 15፡4 ላይ በደንብ ተበራርቷል።

**119፡50 *"መጽናናት"*** ይህ ስም (ቢዲቢ 637) የሚከሰተው እዚህ ጋ እና ኢዮብ 6፡10 ላይ ብቻ ነው፣ ነገር ግን ግሡ (ቢዲቢ 636፣ ኬቢ 688) የተለመደ ነው።

ይህ በመከራ መካከል ላይ ያለ መጽናናት የእግዚአብሔር ቃል ታማኝነት ነው! እርሱ ከታማኝ ተከታዮች ጋር ነው፣ በመከራ፣ በውድቀት፣ በጥቃት፣ በድብርት፣ እና በጥርጣሬ ጊዜ እንኳ ቢሆን (ዘዳ. 31:6፤ኢያ. 1:5፤1 ሳሙ. 12:22፤1 ነገ. 6:13፤8:57፤2 ዜና. 4:9፤ዕብ. 13:5)። እንዴት ላውቅ እችላለሁ፣ ሁኔታዎች የተለየ ቢሆኑ? የእርሱ ቃል! መዝሙር 119፡52 የሚያስታውሰን የእግዚአብሔርን ያለፈ ድርጊት እንድናስብ ነው!

**119፡51** መዝሙረኛው ጥቃት የደረሰበት የእግዚአብሔርን ሕግ ከሚያውቁ ነገር ግን ካልተቀበሉት ሰዎች ነው (መዝ. 119:51ለ፣53)። እውነተኛ እምነት ሊስተዋል የሚችሉ ባሕርያት አሉት። መታዘዝ የሚታይ ማስረጃ ነው፣ የእውነተኛ እምነት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ)።

▣ ***"ወደ ጎን ማለት"*** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ *ቃል የተጠናቀቀ*) ሰፊ የፍች መስክ አለው፣ እናም ዘወትር የሚገልጸው "መዞርጋትን፣" "መንሰራፋትን" ወይም "መቀልበስን" ነው፣ እዚህ ግን የተለየ ዘይቤአዊ ስሜት አለው፣ ከመንገድ የማፈንገጥ፣ የ"እግዚአብሔር መንገድ" ከሚባለው (ማለትም፣ መዝ. 139:24)። የእግዚአብሔር ቃል በግልጽ የተመለከተ መንገድ፣ ፍኖት፣ ፈለግ ነው። መንገዱም ወደ ሕይወት፣ ሰላም፣ ደስታ፣ እና ከእግዚአብሔር ጋር ወደ አለ ኅብረት ያመራል (መዝ. 119:105፤ምሳ. 6:23)። የመጀመሪያው የአኪ ቤተ-ክርስቲያን ሐዋርያት ሥራ ላይ መጠሪያው "መንገድ" ነበር። ማንኛውም ዓይነት ግልጽ ከሆነው ከእግዚአብሔር ቃል መመሪያ ማፈንገጥ ችግሮችን ያመጣል!

የብኪ ፈሊጥ የሆነው "ወደ ቀኝም ወደ ግራም መዞር" (ዘዳ. 5:32፤17:11፣20፤28:14፤ምሳ. 4:27 ላይ ሊታይ ይችላል። በመንገዱ ላይ ቆዩ!

**119፡53** ዘወትር ብኪ ላይ መልካም ሰዎች በጠላቶቻቸው ላይ ቁጣ እንዲወርድ ይጠራሉ ነገር ግን በእውነታው እግዚአብሔርን የሚጠሩት ለቀደመው ቃሉ የታመነ እንዲሆን ነው (ማለትም፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)። ለዚህ ጥሩ ምሳሌ የሚሆነው መዝ. 119፡158 ነው። ቁጣው የተገባው ሆን ተብሎ፣ ታስቦበት ለተደረገ አለመታዘዝ ነው። ኃጢአትና ዓመጻ ውጤት አላቸው፣ በሁለቱም በጊዜ እና በዘላለማዊነት። እግዚአብሔር በሰጠው መንገድ ቆዩ!

**119፡54** ይህ ቁጥር (መዝ. 119፡19) ስለ ሕይወት የሚናገር ይመስላል። የእግዚአብሔር ቃል፣ ለሚያውቁትና ለሚጠብቁት፣ ዕለታዊ፣ የሕይወት ዘመን ዝማሬ ያመጣል (መዝ. 42፡8)! ትዘምራለህን?

**119፡55 *"ስምህ"*** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ።

▣ ***"በሌሊት"*** "ሌሊት" በርካታ ፍችዎች ሊኖሩት ይችላሉ።

1. የማስተያያ ጊዜ
   ሀ. መዝ. 16:7
   ለ. መዝ. 63:6
   ሐ. መዝ. 77:6
2. የጭንቀት ጊዜ – መዝ. 77:2
3. የጸሎት/የምስጋና ጊዜ
   ሀ. መዝ. 42:8
   ለ. መዝ. 92:1-2
   ሐ. መዝ. 119:62
   መ. መዝ. 149:5
   ሠ. ኢሳ. 26:9
   ረ. ማቴ. 14:23፤ ሉቃስ 6:12
   ሰ. ሐዋ. 16:25

▣ ***"ትዕዛዛትህን ጠብቄአለሁና"*** የሌሊት ጊዜ ማስተያየት፣ ጸሎት፣ እና ምስጋና በቀን ጊዜ በየቀኑ መልካም አኗኗር ውጤት መሆን አለበት! መታዘዝ የእምነት ማስረጃ ነው (ሉቃስ 6፡46)።

**119፡56** የመጀመሪያው ስንኝ (መስመር) አሳሚ ነው፣ ምክንያቱም ግልፅ የሆነ ቀዳሚ ባለቤት ስለሌለው።

ሆኖም፣ እሱም ዳግም አጽንዖት የሚሰጠው ለመታዘዝ መሆኑን ተገንዘብ፣ በሁለተኛው ስንኝ! ብዙ ቁጥር ለእግዚአብሔር ራዕይ የተሰጡትን ቃላት አስታውስ (ማለትም፣ ቃል፣ ሕግ፣ ትእዛዛት፣ ሐሳቦች፣ ወዘተ)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ።

***መዝሙር ፡119፡57-64 (ሔት)***

**[57]እግዚአብሔር ክፍሌ ነው**
**ሕግህን እጠብቃለሁ አልሁ።**
**[58]በፍጹም ልቤ ወደ ፊትህ ተማለልሁ**
**እንደ ቃልህ ማረኝ።**
**[59]ስለ መንገዶችህ አሰብሁ፥**
**እግሬንም ወደ ምስክሮችህ መለስሁ።**

**[60]ትእዛዝህን ለመጠበቅ ጨከንሁ**
**አልዘገየሁምም።**
**[61]የኃጥኣን ገመዶች ተተበተቡብኝ**
**ሕግህን ግን አልረሳሁም።**
**[62]ስለ ጽድቅህ ፍርድ፥**
**በእኩለ ሌሊት አመሰግንህ ዘንድ እነሣለሁ።**
**[63]እኔ ለሚፈሩህ ሁሉ፥**
**ትእዛዝህንም ለሚጠብቁ ባልንጀራ ነኝ።**
**[64]አቤቱ፥ ምሕረትህ በምድር ሁሉ ሞላች**
***ሥርዓትህን አስተምረኝ።***

**119፡57 "እግዚአብሔር ክፍሌ ነው"** ይህ ቃል "ክፍል" (ቢ.ዲ.ቢ. 324) በርካታ አጠቃቀሞች አሉት።

1. *ምንም መሬት ለሌዊ አልተደለደለም*
   *ሀ. ዘኍ.* 18፡20
   *ለ. ዘዳ.* 18:2
   *ሐ. ኢያ.* 13:33
   *መ. ሕዝ.* 44:28
2. የተስፋይቱ ምድር ለነገዶች ክፍፍል
   *ሀ. ኢያ.* 17:5፤14፤19:9
   *ለ. ሕዝ.* 47:13
3. እስራኤል እንደ ልዩ ሕዝብ ፣ በሰዎች መካከል
   *ሀ. ኤር.* 10:16
   *ለ. ኤር.* 51:19
4. በእግዚአብሔር የተሰጠ አንደ ነገር፣ ለሁለቱም ለጻድቅና ለኃጢአተኛ
   *ሀ. ኢዮብ* 20:29፤27:13፤31:2
   *ለ. መክ.* 21:20፣21፤3:22፤5:17-18፤9:9
5. በዘይቤአዊነት ጥቅም ላይ የዋለ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ላለ ልዩ የእምነት ግንኙነት
   *ሀ. መዝ.* 16:5፤73:26፤119:57፤142:5
   *ለ. ሰቆ.* 3:24

▣ ***"ቃልህን እጠብቅ ዘንድ ቃል ገባሁ"*** *ይህ ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 1036፣ ኬቢ. 1581) በዚህ አንጓ ባሕርይ የሚያደርገው "ማሰብ"ን ነው (*መዝ.* 119:49-56)።

1. *መዝ.* 119:57 – *ቃል ያልተጠናቀቀ አወቃቀር*
2. *መዝ.* 119:60 – *ቃል ያልተጠናቀቀ አወቃቀር*
3. *መዝ .* 119:63 – *ቃል የድርጊት አንቀጽ*
4. ደግሞም *መዝ.* 119:55 *ተመልከት*

*ታዛዥነት ዋነኛ ነገር ነው! ታዛዥነት ልብን ይገልጻል! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ።*

▣ **119:58 "በፍጹም ልቤ"** *ይህ ፈሊጥ ነው* ከዘዳግም (*ዘዳ.* 6:5፤10:12፤11:13፤13:3፤30:2) *እሱም ሙሉ የሆነ መሰጠትን ያሳያል። ኋላ ላይ በእስራኤል ታሪክ ይህ ሐረግ ጥቅም ላይ ይውል የነበረው*

1. *የዳዊትን ሙሉ ለሙሉ ለእግዚአብሔር መሰጠት ለማሳየት*
2. *የሰሎሞንን በከፊል ለእግዚአብሔር መሰጠት ለማሳየት*

*ለ "ልብ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ።*

▣ *የጸሎት ጥያቄው (ማለትም፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ.* 41:4፤56:1፤57:1) *የተመሠረተው እግዚአብሔር በቃሉ/በተስፋው ላይ ባለው ታማኝነት መሆኑን ተገንዘብ (መዝሙር* 119:41፣ 58፣ 76፣ 116፣ 170)። *የእግዚአብሔር እና የራዕዩ ታማኝነት የመጽሐፍ ቅዱስ እምነት ዋነኛ ዓምድ ነው (አራት ስብከቶችን ተመልከት፣ በመጽሐፍ ቅዱስ እምነት ላይ፣ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር፣ የመጀመሪያ አንቀጽ፣ የተያያዘ* www.freebiblecommentary.org).

**119፡59-60** *ያህዌ ለተስፋው የታመነ እንደተባለ፣ አሁን ደግሞ መዝሙረኛው የእርሱን ታማኝነት ያረጋግጣል (መዝ.* 119:57ለ፣ 61ለ)። *ለእግዚአብሔር ሕግ ፈጣን ምላሽ መስጠት ፍጹም የሆነ መሰጠትን ይገልጻል!!*

*የሁለቱን ግሦች አጽንዖት ተገንዘብ።*

1. *ፈጠንኩ* – ቢ.ዲ.ቢ. 301፣ ኬቢ. 300፣ *ቃል የተጠናቀቀ*
2. *መለስኩ (አሉታዊ)* – ቢ.ዲ.ቢ. 554፣ ኬቢ. 552፣ *ሂዝፓልፔል ያልተጠናቀቀ*

*እግዚአብሔር የተጠራው ፈጣን ምላሽ እንዲሰጥ ነው (መዝ.* 69:17፤79:8፤102:2፤143:7)፣ *እንዲሁ ደግሞ ታማኝ ተከታይ መሆን ይገባዋል ለመንፈስ ቅዱስ ፈጣን ምላሽ ለመስጠት።*

**119:59 "መለስ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ ከዋው ጋር) ሰፊ የፍች መስክ አለው፣ ነገር ግን "ለንስሐ" ጥቅም ላይ የሚውል ቁልፍ ቃል ነው። ስለዚህ፣ አንዳንድ ተንታኞች (ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ 1014) ይሄንን ግሥ የሚመለከቱት የእግዚአብሔርን ሕግ እንደጣሰ ሰው ነው፣ ነገር ግን ተመልሶ የሚጠብቅና እግዚአብሔርን የሚፈራ።

**119:61** መዝሙረኛው ታማኝ ሕይወትን ይኖር ዘንድ ቀላል አልነበረም፣ ምክንያቱም ዘወትር ጠላቶች ስላሉ።

ግሡ (ቢዲቢ 728፣ ኬቢ 795፣ ፒል የተጠናቀቀ) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ የሚተረጎመውም (ኒዶቴ፣ ቅጽ 3 ገጽ 339 ተመልከት)፡

1. አአመመቅ – "ከበቡኝ"
2. አኪጀቅ– "አሰሩኝ"
3. LXX፣ አየተመቅ፣ አኢመቅ – "አጥምደው ያዙኝ"
4. አአቅ – "ወጥመድ ዘረጉብኝ"
5. ጄፒኤስኦኤ – "ተተበተቡብኝ"
6. ፔሺታ – "አጠቁኝ"

ኤቢ (ገጽ 181) ከመዝ. 116:3 ጋር ይዛመዳል፣ እናም እንደተለመደው ስንኙን የሚመለከተው በሰውኛ ዘይቤ ሞትን/መቃብርን እንደሚጠቅስ ነው።

▣ **"ሕግህን አልረሳሁም"** ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ በዚህ መዝሙር ላይ (መዝ. 119:61፣83፣109፣141፣153፣176)። ኃጢአተኛ የእግዚአብሔርን ሕግ ረስቷል (መዝ. 50:22፤119:139)።

**119:62** ይህ የሌሊት ሰዓት ማጠንጠን ከመዝ. 119:55 ጋር ይያያዛል።

**119:63** ታማኝ ተከታዮች በምን ባሕርይ እንደተቀረጹ ተገንዘብ።

1. አንተን የሚፈሩ/የሚያከብሩ
2. ያንተን ራዕይ የሚጠብቁ

ምንም ዓይነት ከእግዚአብሔር ጋር ኅብረት አለኝ ብሎ ማለት አይቻልም፣ እያወቁ ያለ መታዘዝን ሕይወት እየኖሩ።

**119:64** የዚህን ቁጥር ሁለንተናዊ ገጽታ ተገንዘብ። ለ "ምድር" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሬት፣ አገር፣ ምድር።

ቃሉ የተተረጎመው "ምሕረት" በሚል ነው፣ በአአመመቅ ሄሰድ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት (ሄሰድ) እና መዝ. 33:5 ላይ ያለ ማስታወሻ!

▣ **"ሥርዓትህን አስተምረኝ።"** ይህ ሁለተኛው ተተኳሪ ብቻ ነው፣ በዚህ አንጓ ላይ (መዝ. 119:58ለ)። ምንም እንኳ መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ቃል/ተስፋ ቢያሰላስልም፣ እሱ ገና በተሻለ መረዳት ያስፈልገዋል! መደበኛ፣ መንፈስ-ቅዱስ-መር የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ዋነኛ ነገር ነው ለበሰለ፣ በማደግ ላይ ላለ አማኝ (መዝ. 119:12፣26፣64፣108፣124፣135፣171 ተመልከት)!

### መዝሙር ፡119:65-72 (ጤት)

**65አቤቱ፥ እንደ ቃልህ**
**ለባሪያህ መልካም አደረግህ።**
**66በትእዛዛትህ ታምኛለሁና**
**መልካም ምክርና እውቀትን አስተምረኝ።**
**67እኔ ሳልጨነቅ ሳትሁ**
**አሁን ግን ቃልህን ጠበቅሁ።**
**68አቤቱ፥ አንተ ቸር ነህ፥**
**በቸርነትህም ሥርዓትህን አስተምረኝ።**
**69የትዕቢተኞች ዓመፅ በላዬ በዛ**
**እኔ ግን በፍጹም ልቤ ትእዛዛትህን እፈልጋለሁ።**
**70ልባቸው እንደ ወተት ረጋ**
**እኔ ግን በሕግህ ደስ ይለኛል።**
**71ሥርዓትህን እማር ዘንድ**
**ያስጨነቅኸኝ መልካም ሆነልኝ።**
**72ከአእላፋት ወርቅና ብር ይልቅ**
**የአፍህ ሕግ ይሻለኛል።**

**119:65** ይህ ቁጥር የታማኝ ተከታይን ርዕዮተ-ዓለም ያጠቃልላል። የእግዚአብሔርን ራዕይ ማወቅ (መዝ. 119:66) እና መታዘዝ (መዝ. 119:67፣69) ደስተኛ፣ ጤናማ፣ ሰላማዊ ሕይወትን ያመጣል። እውነተኛ ሕይወት የሚገኘው በእርሱ ብቻ ነው። በዚህ መዝሙር ላይ የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ እግዚአብሔርን ራሱን ከማወቅ ጋር እኩል መሆኑን አስታውስ!

ከሞላ ጎደል የዚህ መዝሙር እያንዳንዱ ቁጥር የዕብራይስጥ ቃል አለው፣ የእግዚአብሔርን ራዕይ የሚገልጽ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ)።

የዕብራይስጡ ቃል טוב (ቢዲቢ 373) መዝ. 119:65፣ 66፣ 68፣71፣ እና 72 ቁጥሮችን ይጀምራል። እሱም የዚህ አንጓ ቁልፍ ቃል ነው።

**119:66** ምንም እንኳ መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ራዕይ ቢያውቅም፣ እጅግ በተሻለ መረዳት እንደሚኖርበት ተገንዝቧል (መዝ. 119:68፣ ሁለቱም ግሦች "ማስተማር፣" ቢዲቢ 540፣ ኬቢ 531፣ ፒል ተተኳሪ ናቸው፣ ማለትም፣ የጸሎት ጥያቄ፣ መዝ. 119:12፣26፣64፣66፣68፣108፣124፣ 135፣171)።

▣ **"አምናለሁ"** በርካታ የተጠናቀቁ ግሦች አሉ፣ የመዝሙረኛውን ዝንባሌ የሚገልጹ።

1. አምናለሁ – ቢዲቢ 52፣ ኬቢ 63፣ ሂፊል የተጠናቀቀ (ልዩ ርዕስ ተመልከት: ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ)
2. እጠብቃለሁ – ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ ቃል የተጠናቀቀ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ)
3. ደስ ይለኛል – ቢዲቢ 1044፣ ኬቢ 1613፣ ፒልፓል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 1:2፤112:1፤119:16፣24፣35፣ 47፣70፣77፣92፣143፣174

የአእምሮ ዕርገት (ወደ ላይ ማሰብ) ከታዛዥነት ሕይወት ጋር እንዴት መግጠም እንዳለበት ተገንዘብ (ያዕቆብ 1:22-25)።

**119:67** መዝሙረኛው ባለፈው ጊዜ የነበረበትን አለመታዘዝ ተናዝዟል፣ ይኸውም የእግዚአብሔርን ተግሣጽ ያስከተለበት። የእግዚአብሔር ተግሣጽ የሚወድድ ወላጅ ድርጊት ነው (ዕብ. 12:5-13)። ይህ የሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30 ርግማን የእግዚአብሔር ምላሽ ነው፣ ለኪዳን አለመታዘዝ፣ እናም የእርሱ ሐሳብ ለተከታዮቹ፣ መንገዳቸውን እንዲቀይሩ ነው! እሱ ሊባርከን ይሻል! ተግሣጽ ዘወትር የመቤዠት ዓላማ አለው!

**119:68** ይህ የቅኔው የመጀመሪያ ስንኝ የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ባሕርይ ነው። እሱ "መልካም" ነው (ቢዲቢ 373 II፣ መዝ. 25:8፤86:5፤ 100:5፤106:1፤ኤር. 33:11፤ናሆ. 1:7)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት።

▣ ***"ሥርዓትህን አስተምረኝ።"*** ይህ ሁለተኛው አጠቃቀም ነው፣ የዚህ ፒል ተተኳሪ ግሥ (መዝ. 119:66)። እግዚአብሔር ራሱንና ፍቃዱን በቅዱስ ቃሉ ውስጥ መግለጥ ይሻል።

**169:69 -70** በመዝሙራት ላይ ተደጋጋሚ ጉዳይ እንደሆነው፣ መዝሙረኛው እንደተጠቃ ተሰምቶታል። ትዕቢተኛ ስለ እርሱ ዋሽቷል። ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ አስቸጋሪ ነው፣ እነዚህ አጥቂዎች እነማን እንደሆኑ። እነርሱ ዘወትር በኅብረተሰቡ ውስጥ ሃብታሞችና ብርቱዎች ናቸው፣ እዚህ እንደሆነው (ማለትም፣ "ስብ፣" ቢዲቢ 316፣ መዝ. 119:70ሀ፣ መዝ. 17:10፤73:7፤ይኸም ከመንፈሳዊነት አኳያ ከኢሳ. 6:10፣ ቢዲቢ 1031 I ጋር ትይዩ ነው)። ነገር ግን ለመዝሙረኛው እውነተኛ ብልጥግና እግዚአብሔርንና የእርሱን ራዕይ ማወቅ ነው (መዝ. 119:72፣ ዝኪ. 19:10)።

**119:69** ግሥ (ቢዲቢ 381፣ ኬቢ 378፣ ቃል የተጠናቀቀ) ስንኝ 1 ላይ የሚለው መለጠፍ ወይም ስም ማጥፋት ነው (ኢዮብ 13:4)። ይህ አንጓ ሁለት ያልተጠናቀቁዎች አሉት፣ እነርሱም የመዝሙረኛውን በሂደት ላይ ያለ ድርጊት የሚገልጹ።

1. እፈልጋለሁ፣ መዝ. 119:69 – ቢዲቢ 665፣ ኬቢ 718፣ ቃል ያልተጠናቀቀ
2. እማራለሁ፣ መዝ. 119:71 – ቢዲቢ 540፣ ኬቢ 531፣ ቃል ያልተጠናቀቀ

**119:70 "ልብ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ።

**119:70ለ** "ነገር ግን" የሚል የለውም፣ በዕብራይስጡ ጽሑፍ። ሆኖም፣ የሰላ ተቃርኖ ተመልክቷል። "ሁለቱ መንገዶች" የ ዘዳ. 30:15-20 እና መዝ. 1:1 ተመልክተዋል።

**119:71** መዝሙረኛው እውቅና ሰጥቷል፣ የእግዚአብሔር ተግሣጽ ለጥቅም እንደሆነ፣ ምክንያቱም እሱ ወደ እግዚአብሔር እና ወደ ቃሉ እንዲመለስ ስላደረገው። የሕይወት ፍትሐዊ አለመሆን፣ የግል ምርጫዎች ውጤት አስፈሪ መሆን ዘወትር ዕድሎች (ጥሩ አጋጣሚዎች) ናቸው፣ በይበልጥ እግዚአብሔርን ለመታመን። በዚህ ሐሳብ ዙሪያ የረዳኝ መጽሐፍ የሐናህ ዊዛል ስሚዝ የክርስቲያን ደስተኛ ሕይወት ምሥጢር።

## መዝሙር :119:73-80 (ዮድ)

**[73]እጆችህ ሠሩኝ አበጃጁኝም**
**እንዳስተውል አድርገኝ፥ ትእዛዛትህንም እማራለሁ።**
**[74]በቃልህ ታምኛለሁና**
**የሚፈሩህ እኔን አይተው ደስ ይላቸዋል።**
**[75]አቤቱ፥ ፍርድህ ጽድቅ እንደ ሆነች፥**
**በእውነትህም እንዳስቸገርኸኝ አወቅሁ።**
**[76]ምሕረትህ ለመጽናናቴ ትሁነኝ፥**
**እንደ ቃልህም ለባሪያህ ይሁነው።**
**[77]ሕግህ ተድላዬ ናትና**
**ቸርነትህ ትምጣልኝ፥ በሕይወትም ልኑር።**
**[78]ትዕቢተኞች በዓመፅ ጠምመውብኛልና ይፈሩ**
**እኔ ግን በትእዛዝህ እጫወታለሁ።**
**[79]የሚፈሩህና**
**ምስክሮችህን የሚያውቁ ወደ እኔ ይመለሱ።**
**[80]እንዳላፍር**
**ልቤ በሥርዓትህ የቀና ይሁን።**

**119:73** ይህ ቁጥር እግዚአብሔር መዝሙረኛውን እንደፈጠረው ያስረግጣል። ይህም በብዙ መንገዶች ተገልጿል።

1. የዘፍ. 2:7 ጠቃሽ ("ማበጀት" [አካል] – ቢዲቢ 427፤"የተሠሩ ቀናት" – መዝ. 135:16)

2. *እጆችህ ሠሩኝ* – ቢዲቢ. 793 1፣ ኢዮብ 10:8፤31:15፤መዝ. 139:15
3. *የእጆችህ ሥራ* – ኢዮብ 10:3፤14:15፤መዝ. 138:8
4. *ሁለቱም ግሦች ዘዳ. 32:6 ላይ ይገኛሉ፣ እናም የተጠቃለለውን እስራኤል ያመለክታሉ*

ሰዎች ልዩ ፍጥረት ናቸው፣ በእግዚአብሔር መልክና አምሳል የተፈጠሩ (ዘፍ. 1:26-27) ለኅብረት (ዘፍ. 3:8)። እያንዳንዱ ልዩ ፍጡር ነው (መዝ. 139:14-16)። ይሄንን መረዳት መጽሐፍ ቅዱሳዊ ርዕዮተ-ዓለም ነው! እኛ የነሲባዊ ሁነቶች ወይም ሂደቶች ውጤት አይደለንም። በእያንዳንዱ ግለሰብ ፍጥረት ላይ ዓላማ አለ።

▣ **"እንዳስተውል አድርገኝ፥"** ይህ ብቸኛው ተተኳሪ (መዝ. 119:73-80) የጸሎት ጥያቄ ነው፣ በዚህ አንጓ ላይ (ቢዲቢ. 106፣ ኬቢ. 122፣ *ሂፊል ተተኳሪ*)፣ ነገር ግን በርካታ ተጽዕኖዊዎች አሉ።

እግዚአብሔር ብቻ ነው የወደቀውን ሰው አእምሮ ሊከፍት የሚችለው፣ እንዲማር (ቢዲቢ. 540፣ ኬቢ. 531፣ *ቃል ተጓዳኝ*) ስለ እርሱ (እግዚአብሔር) የእርሱን ራዕይ በማስተዋል። ይህ መማር (እንደ ሼማ ግሥ፣ ዘዳ. 6፡4-9) የሚያመለክተው የየዕለቱን የሕይወት ስልት ትግበራ ነው፣ የእግዚአብሔር ራዕይ።

**119፡74 "ዘንድ"** ይህ የተጽዕኗዊ አወቃቀር ምልክት ነው (መዝ. 119:74፣76፣77፣78፣70፣80)። እነዚህ ደግሞ የጸሎት ጥያቄዎችን ያንጸባርቃሉ።

በዚህ ቁጥር ላይ ሁለት አሉ።

1. *መመልከት* – ቢዲቢ. 906፣ ኬቢ. 1157፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
2. *መደሰት* – ቢዲቢ. 970፣ ኬቢ. 1333፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*

እነዚህ እውነታዎች ከመዝሙረኛው ... ጋር እንደተያያዙ ተገንዘቡ

1. ትዕግሥት ("መጠበቅ፣" "ተስፋ፣" መዝ. 119:74ለ)
2. የእግዚአብሔርን ራዕይ ማወቅ (መዝ. 119:75)
3. መለኮታዊ መከራ (119:75፤67፣71)

"መጠበቅ" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ. 403፣ ኬቢ. 407፣ *ፒል የተጠናቀቀ*) ትዕግሥትን ይገልጻል። ይህ ግሥ ዘወትር የሚጠቅሰው ተስፋ/ትዕግሥት በእግዚአብሔር በራሱ ነው (ኢዮብ 13:15፤መዝ. 31:24፤33:22፤38:15፤39:7፤42:5፣11፤43:5፤69:3፤130:7፤131:3)፣ ነገር ግን መዝሙር 119 ላይ የእግዚአብሔር ራዕይ መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ) ለእግዚአብሔር ለራሱ ተዘዋውሯል። እነርሱ አንድ ናቸው። የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ማለት እግዚአብሔርን ማወቅ ነው። አንደኛው አስረጅ ነው፣ ሌለኛውም ግንኙነታዊ ነው፣ ነገር ግን እነርሱ አንድ ላይ መሄድ አለባቸው!

**119፡75 "በእውነትህም እንዳስቸገርኸኝ አወቅሁ።"** እግዚአብሔር ለቃሉ እውነት ነው እንዲሁም ለዓላማውም የታመነ ነው፣ ለታማኝ ተከታዮቹ። በፍጥረት ላይ ትልቅ ዓላማ አለ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ። "መከራ" እንኳ ቢሆን የመዳረሻ ዓላማ አለው (ሰቆ. 3:19-38፤ዕብ. 5:8፤12:1-13)። የደኅንነት ግቡ ወደፊት ለሚሆን አቋም/ስፍራ ኅብረት አይደለም ነገር ግን የአሁን የቅርብ ወዳጅነት እንጂ፣ ይኸውም የያህዌ ተከታዮችን ቤተሰብ ባሕርያት የሚያንጸባርቅ፣ እሱ ለፈጠራቸው፣ ነገር ግን በውድቀት ምክንያት እስካሁን ላላወቁት!

መታወስ የሚኖርበት በዚህ ሕይወት ላይ ያለ ችግር በርካታ ታሳቢ መነሻ/ዓላማዎች ሊኖሩት እንደሚችል ነው።

1. በኃጢአት ላይ የሚሆን ፍርድ፣ ከያህዌ ጋር የሚኖርን ግንኙነት ለመመለስ ወይም ለማነሣሣት (መዝ. 69፡26)
2. የውድቀት ውጤት። ክፉው ወደ ምድራችን ገብቷል። ክፉ ነገሮች ይሆናሉ፣ የእግዚአብሔር ፍቃድ ያልሆኑ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መከራ)።
3. እነርሱ እግዚአብሔርን እንድንታመን ያደርጉናል፣ እናም እምነታችንን ለማሳደግ (ሮሜ. 5:3-5፤ዕብ. 5:8፤12:10-11)

የትኛው እንደሆነ ፈጽሞ ባላውቅም፣ ቁ. 3 ላይ ማተኮርን እመርጣለሁ! የእኔ ርዕዮተ-ዓለም ምንም ነገር እንዲያው በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እንደማይሆን ነው!

▣ **"ፍርዶች"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዳኛ፣ ፍርድ፣ ፍትሕ።

▣ **"ጽድቅ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ።

**119፡76 "ምሕረትህ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት (ሄስድ)።

▣ **"እንደ ቃልህ"** ይህ ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው (መዝ. 119፡65)። እግዚአብሔር እውነት ነው ለራዕዩ።

**119፡77 "ሕግህ ተድላዬ ናትና"** ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 119፡70 ላይ።

**119:78ሀ** ይህ የሚያንጸባርቀው መዝ. 119:69-70 ነው። ትዕቢተኛ ያፍራል (ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 119:6 ላይ)፣ ነገር ግን ታማኙ መዝሙረኛ ሳይሆን (ዝከ. 119:80)።

**119:78ለ "እኔ ትእዛዛትህን አሰላስላለሁ"** ታማኝ ተከታዮች ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ጊዜ ያሳልፋሉ። ያጠናሉ፣ ያሰላስላሉ፣ እናም የሚለውን ለመተግበር ይሞክራሉ። ሐሳቦቻችን ድርጊቶቻችን ይሆናሉ። ማሰላሰል በራዕይ ላይ ዓይነተኛ ነገር ነው (መዝ. 1:2፤119:15፣23፣48፣78፣97፣148)። ምን ያህል ጊዜ ከእግዚአብሔር ቃል ጋር ያሳልፋሉ?

**119፡79** ይህ ቁጥር የሚያስረግጠው እውነት፣ እግዚአብሔርን የሚፈልጉ፣ እንከተለዋለን በሚሉት ውስጥ ሊመለከቱት እንደሚገባ ነው።

▣ **"የሚያውቁ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ።

**119:80 "ያለ ነውር"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ያለ ነውር፣ ንጹሕ፣ ያለ በደል፣ እና ያለ ነቀፋ።

**መዝሙር :119:81-88 (ካፍ)**

[81]**ነፍሴ መድኃኒትህን ናፈቀች**
**በቃልህም ታመንሁ።**
[82]**መቼ ታጽናናኛለህ እያልሁ**
**ዓይኖቼ ስለ ቃልህ ፈዘዙ።**
[83]**በጢስ እንዳለ አቁማዳ ሆኛለሁና**
**ሥርዓትህን ግን አልረሳሁም።**
[84]**የባሪያህ ዘመኖች ስንት ናቸው?**
**በሚያሳድዱኝስ ላይ መቼ ትፈርድልኛለህ?**
[85]**ኃጢአተኞች ጨዋታን ነገሩኝ፥**
**አቤቱ፥ እንደ ሕግህ ግን አይደለም።**
[86]**ትእዛዛትህ ሁሉ እውነት ናቸው**
**በዓመፅ አሳድደውኛል እርዳኝ።**
[87]**ከምድር ሊያጠፉኝ ጥቂት ቀርቶአቸው ነበር**
**እኔ ግን ትእዛዛትህን አልተውሁም።**
[88]**እንደ ምሕረትህ ሕያው አድርገኝ**
**የአፍህንም ምስክር እጠብቃለሁ።**

**119:81-88** ይህ አንጓ በተጠናቀቁ ጊዜ ግሦች ተሞልቷል። መዝሙረኛው እንደተጠቃ ተሰምቶታል!

1. የሚያሳድዱኝ፣ መዝ. 119:84
2. ትዕቢተኞች ጉድጓድ ቆፈሩልኝ፣ መዝ. 119:85
3. በሕግህ የማይሄዱ ሰዎች፣ መዝ. 119:85
4. እነርሱ በሐሰት አሳደዱኝ፣ መዝ. 119:86
5. እነርሱ ከምድር ሊያጠፉኝ ጥቂት ቀርቷቸው ነበር፣ መዝ. 119:87

እሱ ለእግዚአብሔር ቃል ታማኝ መሆኑን አስረግጧል፣ እናም እግዚአብሔርን ይለምናል፣ በእርሱ ጎን እንዲሠራ።

1. እርዳኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 740፣ ኬቢ. 810፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 119:86
2. አድሰኝ/ጠብቀኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 1036፣ ኬቢ. 1581፣ *ፒል ተተኳሪ*፣ መዝ. 119:88

**119:81 "ነፍሴ"** ይህ ቃል *ኔፊሽ* ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 659)። ለሙሉ ማብራሪያ ዘፍ. 35:18 ላይ ማስታወሻ ተመልከት፣ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር www.freebiblecommentary.org.

▣ **"ናፈቀች"** መዝሙረኛው በርካታ ግሦችን ይጠቀማል፣ ያለበትን አካላዊና አእምሯዊ አቋም ለመግለጽ።

1. ናፈቀች – ቢ.ዲ.ቢ. 477፣ ኬቢ. 476፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 119:81
2. ይጠብቃል – ቢ.ዲ.ቢ. 403፣ ኬቢ. 407፣ ፒል የተጠናቀቀ፣ መዝ. 119:81
3. ዓይኖቼ ፈዘዙ – ቢ.ዲ.ቢ. 477፣ ኬቢ. 476፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ መዝ. 119:82
4. በጭስ ላይ እንዳለ አቁማዳ ሆንኩ – ቢ.ዲ.ቢ. 224፣ ኬቢ. 243፣ *ቃል* የተጠናቀቀ። ይህ ያልተለመደና የአልፎ አልፎ ፈሊጥ ነው። እሱም የሚለው "የተቃጠለ" እና "የደረቀ" ነው። ነገር ግን ከቀጣዩ ስንኝ የተነሣ እሱ የሚገልጸው በጭስ የተነሣ ዕውርነት ነው (1 ቆሮ. 13:12)።

**119:82** በሕይወት ችግሮችና በግል ጥቃቶች መካከል፣ ታማኝ ተከታዮች እንኳ ወደ እግዚአብሔር ይጣራሉ፣ "ለምን?" ወይም "መቼ ያበቃል?" በሚል።

**119:83** የመዝሙር 119:83ሀ ፈሊጥ ያልተለመደና አሻሚ ነው (ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 119:81፣ ቁ. 4)።

ሁለተኛው ስንኝ መዝሙረኛው የገዛ ራሱን ታማኝነት ለማስረገጥ የሞከረበት ነው (መዝ. 119:81ለ፣ 87ለ፤ደግሞም መዝs. 119:61፤141፤153፣ 176 እይ)። የእርሱ አሳዳጆች የእግዚአብሔር ፍርድ ይገባቸዋል፣ እሱ ግን አይገባውም። ራሱን በእግዚአብሔር ታማኝነት ላይ ጥሏል (መዝ. 119:88ሀ)።

**119:84 "የባሪያህ ዘመኖች ስንት ናቸው?"** ይህ የሚያስረግጠው

1. የእግዚአብሔርን ቀድሞ አዋቂነት (ማቴ. 10:29-31)
2. የሰው ልጅ ሕይወት የተወሰነ ጊዜ (መዝ. 39:4)
3. እያንዳንዳችን ባለን ሰዓት በአግባቡ የመጠቀም ጥሪ (መዝ. 90:12፤ማቴ. 6:25-34፤ኤፌ. 5:15-16)

**119:85 "ጉድጓድ ቆፈሩ"** ይህ የአደን ፈሊጥ ነው። ጉድጓድ ይቆፈር ነበር፣ ታዳኙን ለመያዝ። እሱም ለሰው ልጅ ተንኮለኝነት ዘይቤ ሆነ (መዝ. 7:15፤57:6፤ኤር. 18:22)።

አእመቅ እና የተእመቅየዕብራይስጡን ሥር "ተረት" በሚል ነው የሚመለከቱት (ቢ.ዲ.ቢ. 967) በ "ጉድጓድ" ፈንታ (ቢ.ዲ.ቢ. 1001)። ይህ ከ

**ዐ**ወደ **ዐ**የሆነ ለውጥ ነው።

**119:86** "ትእዛዛቱ" እዚህ የሚያመለክቱት "ርግማኖችን" ይሆናል፣ በተገለጠው በእግዚአብሔር ፍቃድ ባመጹት ላይ (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)። እነዚህ አሳዳጆች ናቸው፣ መዝ. 119:85ለ የተመለከቱት፣ እነርሱም በእግዚአብሔር ሕግ በተገቢው የማይኖሩ።
እነርሱ ቀጥተኛ ተቃራኒዎች ናቸው፣ የታማኝ ተከታዮች (መዝ. 119:81፣82፣83፣87)።

▣ ***"ዕርዳኝ"*** ይህ ተተኳሪ (መዝ. 119:81-88 ማስታወሻ ተመልከት) ከመዝ. 109:26 ጋር ተመሳሳይ ነው። የእግዚአብሔር የኪዳን ታማኝነት (ማለትም፣ ሄስድ፣ መዝ. 119:88ሀ፤ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት) የሰው ልጅ ተስፋ መሠረት ነው። የእርሱ የማይለወጥ የምሕረትና የጸጋ ባሕርይ ነው ተስፋንና ሰላምን በዚህ በወደቀ ዓለም የሚያመጣ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት።

**119:88ሀ** የዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 1022) እንደሚጠቅሰው ኤምቲ እና LXX "ሕይወቴን ጠብቅ" የሚል ግሥ ሲኖራቸው (ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ ፒል ተተኳሪ)፣ ሙባጥ ጽሑፍ (ሙት ባሕር ጥቅሎች) "እዘንልኝ" የሚል አለው (አእት)።

**119:88ለ** ይህ የእግዚአብሔር ታማኝ ተከታዮች መሻት ነው (መዝ. 19:14)!
"መጠበቅ" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581) ,ቃል ተጓዳኝ ነው።ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ። ለራዕይ መታዘዝ ዋነኛ ነገር ነው፣ እናም አንዱ ከእግዚአብሔርና ከመሲሑ ጋር ላለው የእምነት ግንኙነት ማስረጃ ነው (ሉቃስ 6:46)።

***መዝሙር :119:89-96 (ላሜድ)***

**89 አቤቱ፥ ቃልህ በሰማይ**
**ለዘላለም ይኖራል።**
**90 እውነትህ ለልጅ ልጅ ናት**
**ምድርን መሠረትሃት እርስዋም ትኖራለች።**
**91 ሁሉም ባሪያዎችህ ናቸውና**
**ቀኑ በትእዛዝህ ይኖራል።**
**92 ሕግህ ተድላዬ ባይሆን፥**
**ቀድሞ በጕስቍልናዬ በጠፋሁ ነበር።**
**93 በእርሱ ሕያው አድርገኸኛልና**
**ፍርድህን ለዘላለም አልረሳም።**
**94 እኔ የአንተ ነኝ**
**ፍርድህን ፈልጌአለሁና አድነኝ።**
**95 ኃጢአተኞች ያጠፉኝ ዘንድ ጠበቁኝ**
**ምስክርህን ግን መረመርሁ።**
**96 የሥራህን ሁሉ ፍጻሜ አየሁ**
**ትእዛዝህ ግን እጅግ ሰፊ ነው።**

**119:89 "ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (ኦላም)።

▣ **"አቤቱ ጌታ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ ***"ቃልህ በሰማይ ይኖራል"*** የግሡ (ቢዲቢ 662፣ ኬቢ 714፣ ኒፋል አንቀጽ) መሠረታዊ ፍች "መቆም" ነው። ይህ ብቸኛው የዚህ ግሥ አጠቃቀም ነው፣ በዚህ ፈሊጥ።
የእግዚአብሔር የተደራጀ/የጸና የፍጥረት ሐሳብ (ኢሳ. 54:18) የመዝ. 119:90-91 ግፊት ነው (የተለየ ግሥ፣ ቢዲቢ 763፣ ኬቢ 840)። "የቆሙትን" ነገሮች ተገንዘቡ።
1. የእግዚአብሔር ቃል (መዝ. 119:89ለ፣ 91ሀ)
2. የያህዌ ታማኝነት
3. የያህዌ ፍጥረት
እነርሱ ሁሉ የእርሱ አገልጋዮች ናቸው (መዝ. 119:91ለ)። ነገር ግን መዝ. 119:96 ተቃርኖ እንደሚያመለክት ተገንዘብ። ሆኖም፣ የተቃርኖው ግፊት ርግጠኛ አይደለም።

**119:90ሀ** ይህ እውነት ከመዝ. 36:5 እና 89:1-2 ጋር ትይዩ ነው። እነርሱም ስለ እግዚአብሔር፣ ስለ ቃሉ፣ እና ስለ ፍጥረት ዘላለማዊነት ይናገራሉ። የታማኝነት ባሕርያትም
1. እግዚአብሔር ራሱ
2. የእርሱ በቃል መገለጥ
3. የእርሱ በፍጥረት መገለጥ (መዝ. 119:91፤148:1-6፤ኤር. 31:35-37)

**119:91 *"ሁሉም ባሪያዎችህ ናቸውና"*** ይህ ፈሊጥ የሚያመለክተው ወደ ተፈጠሩ ነገሮች ሁሉ ነው (ማለትም፤ዘፍጥረት 1፣ መዝ. 103:19፤መክ. 11:5፤ ኤር. 10:16፤51:19)። የእግዚአብሔር ቃል ሥጋን ወደ ሕላዌ አምጥቶታል፣ ይደግፈዋልም። ሥጋዊው ወሰን አለው (መዝ. 119:96)፣ የእግዚአብሔር ቃል ግን ወሰን የለውም።

**119፡92 “እንደ”** የሚከተሉትን ዓረፍተ-ነገሮች ሁኔታዊ ጠባይ ተገንዘብ፣ ስለ መዝሙረኛው፣ እሱም መባንን/መታደስን እና የእግዚአብሔርን ራዕይ የሚሻ፣ ይኸውም ዘላለማዊ የሆነውን። “እኔ” የሚለውን ብዛት መዝ. 119፡92-96 ላይ ተገንዘብ፣ አአመመቅ (6) እሱም የመዝሙረኛውን ሐሳብና ድርጊቶች የሚገልጽ።

**119፡93 “ፍርድህን ለዘላለም አልረሳም።”** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 119፡83ለ ላይ።

▣ **“በእርሱ ሕያው አድርገኸኛልና”** ይህ *ግሥ* ፔል የተጠናቀቀ ነው፣ እሱም የእግዚአብሔርን የተጠናቀቀ የማዳን *ሥራ* የሚያመለክት። ይህ ከመዝ. 119፡88 ጋር በተቃርኖ ተመልክቷል።

**119፡94 “እኔ የአንተ ነኝ”** መዝሙረኛው ያስረግጣል፣ እንደ ፍጥረት፣ እሱ የያህዌ መሆኑን፣ የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ፣ የእርሱን ዓላማ የሚታዘዙትን።

▣ **“አድነኝ”** ይህ *ሂፊል* ተተኳሪ ነው፣ በዚህ አንጓ ላይ ብቸኛው ተተኳሪ። ልዩ ርዕስ ተመልከት: ደኅንነት (ብኪ)። መዝሙረኛው እንደተጠቃ ተሰምቶታል (መዝ. 119:95ሀ)። መዝ. 119:92 ላይ “ጉስቍልና” የሚለው ቃል ሊያመለክት የሚችለው የ “ክፉውን” ወኪል ወይም እግዚአብሔርን ነው (መዝ. 119:67፤71)።

ያህዌ የሚፈልጉትን/የሚታመኑትን ያድናቸዋል (መዝ. 13:5፤25:2፤31:14፤52:8፤56:4፤86:2)። ሁለት ዓይነት የኪዳን ገጽታዎች አሉ (መለኮታዊ እና የግለሰብ ሰዎች)!

▣ **“ፍርድህን ፈልጌአለሁና”** ይህ የታማኝ ተከታዮች ሐሳብ በንቃት ይፈልጋል (ቢዲቢ 205፣ ኬቢ 233፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) የእግዚአብሔር ራዕይ ደግሞ ይገኛል መዝ. 119:2፤45፤155 ላይ። ራዕይ መለኮታዊ ገጽታ አለው እንዲሁም ራዕይ ግለሰባዊ ገጽታ አለው!

**119፡96** ይህ ቁጥር ለመረዳት አስቸጋሪ ነው። ሆኖም፣ “የተወሰነ” ምንም ይሁን (የፍጥረትን ሥርዓት የሚያመለክት ይመስላል) እሱ ከእግዚአብሔር ዘላለማዊ (“ሰፊ” ራዕይ ጋር የሚቃረን ይመስላል (ማለትም፣ ወሰን የለውም)።

“ፍጽምና” የሚለው ቃል (ቢዲቢ 479) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው።

መዝሙረኛው ዘላለማዊውን ይጠራል፣ እንዲያድነው። ኃጢአተኞች ይጠፋሉ፣ ፍጥረት ይጠፋል (ማለትም፣ 2 ጴጥ. 3፡10፤12)፣ ነገር ግን ዘላለማዊው ታማኝ ተከታዮቹን ያስታውሳቸዋል!

### መዝሙር ፡119፡97-104 (ሜም)

**97 አቤቱ፥ ሕግህን እንደ ምን እጅግ ወደድሁ!**
**ቀኑን ሁሉ እርሱ ትዝታዬ ነው።**
**98 ለዘላለም ለእኔ ነውና**
**ትእዛዝህ ከጠላቶቼ ይልቅ አስተዋይ አደረገኝ።**
**99 ምስክርህ ትዝታዬ ነውና**
**ካስተማሩኝ ሁሉ ይልቅ አስተዋልሁ።**
**100 ትእዛዝህን ፈልጌአለሁና**
**ከሽማግሌዎች ይልቅ አስተዋልሁ።**
**101 ቃልህን እጠብቅ ዘንድ**
**ከክፉ መንገድ ሁሉ እግሬን ከለከልሁ።**
**102 አስተምረኸኛልና**
**ከፍርድህ አልራቅሁም።**
**103 ቃልህ ለጕሮሮዬ ጣፋጭ ነው**
**ከማርና ከወለላ ይልቅ ለአፌ ጣፈጠኝ።**
**104 ከትእዛዝህ የተነሣ አስተዋልሁ**
**ስለዚህ የሐሰትን መንገድ ጠላሁ።**

**119፡97 “አቤቱ፥ ሕግህን እንደ ምን እጅግ ወደድሁ!”** በብዙ መንገዶች መዝሙር 19 እና 119 ሥነ-መለኮታዊ ተቃራኒዎች ናቸው፣ ከታሪካዊ መጻሕፍትና ከትንቢታዊ መጻሕፍት አቅርቦት (ጽሑፍ) ጋር፣ እስራኤል በእግዚአብሔር ራዕይ ላይ እንዴት እንዳደረገ።

ፍቅር (ቢዲቢ 12፣ ኬቢ 17፣ *ቃል* የተጠናቀቀ፣ መዝሙር 119:47፣ 48፣ 113፣ 127፣ 163፣ 165) ባሕርይ ያደረገው “ቀኑን ሙሉ ማሰላሰል” ነው (መዝ. 119:15፤48፤99)።

መውደድ ማለት (ዘዳ. 6:5)

1. አብሮ ጊዜ ማሳለፍ
2. መደሰት
3. መታዘዝ
4. ወደ ሌሎች ማስተላለፍ ነው

በአአመመቅ የተተረጎመው ሐረግ “ቀኑን ሁሉ” የዕብራይስጡ ቃል *ኦላም* ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (*‘ኦላም*)

**119፡98** የእግዚአብሔርን ራዕይ ማወቅ ታማኝ ተከታዩን ብልህ ያደርገዋል

1. ከጠላቶቹ ይልቅ፣ መዝ. 119፡98
2. ከአስተማሪዎቹ ይልቅ፣ መዝ. 119፡99

3. ከሽማግሌዎች ይልቅ (ማለትም፣ ልምድ ካላቸው)፣ መዝ. 119፡100

**119፡100** ጥበብ እንዲያው እውቀት ሳይሆን የሕይወት ስልት መታዘዝ እንደሆነ ተገንዘብ (መዝ. 119:100ለ)። ይህ መታዘዝም ተገልጿል እንደ

1. ከክፉ መንገድ ሁሉ እግሬን ከለከልሁ (መዝ. 1:1፤5:8፤16:11፤139:24፤ምሳ. 1:15፤4:14)
2. ከፍርድህ አልራቅኩም (ከእግዚአብሔር የተገለጠ መንገድ ለሚደረግ ማፈንገጥ የሆነ ፈሊጥ፣ ዘዳ. 17:20፤ኢያ. 23:6)

የቤተ-ክርስቲያን የመጀመሪያ ስም "መንገድ" ነበር (ሐዋ. 9:2፤18:25፣26፤19:9፣23፤22:4፤24:14፣ 22)።

**119፡101ለ "ቃልህን እጠብቅ ዘንድ"** ይህ ቁልፍ ሥነ-መለኮታዊ እውነት ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ።

**119፡102ለ** መዝሙር 119 ላይ እግዚአብሔርና የእርሱ ራዕይ ተዋህደዋል። እሱን ማወቅ ማለት ቃሉን ማወቅ ነው። እግዚአብሔር የራዕይ መምህርና ይዘት ነው። መዝሙረኛው እግዚአብሔር እንዲያስተምረው ያቀረበው ጥያቄ መዝ. 119:12፣26፣33፣ 64፣108፣124፣135፣171 ላይ ይገኛል።

**119፡103** ይህ ቁጥር የሚያንጸባርቀው መዝ. 19:10ለን ነው፣ ነገር ግን ለ "ጣፋጭ" በተለየ ቃል (ቢዲቢ 576፣ ኬቢ 594፣ ኒፋል የተጠናቀቀ፣ "ለስላሳ" እዚህ ጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ)። "ጣፋጭነት" የሚለው ፈሊጥ የእግዚአብሔር ትምህርት እንዴት ሕይወትን አስደሳችና ሰላማዊ እንደሚያደርገው መግለጫ መንገድ ነው!

**119፡104** አንድ ብቻ ትክክለኛ የእውነት፣ የሕይወት፣ የሰላም፣ እና የደስታ ምንጭ አለ — ያህዌ። እሱን ማወቅ ማለት ሌሎቹን መንገዶች ሁሉ ፈጽሞ መተው ነው ("መጥላት") (ማለትም፣ መዝ. 119:53፣128፣163፤ ምሳ. 13:5፤ አሞጽ 5:15)።

**መዝሙር ፡119፡105-112 (ኖን)**

**105ሕግህ ለእግሬ መብራት፥**
**ለመንገዴ ብርሃን ነው።**
**106የጽድቅህን ፍርድ እጠብቅ ዘንድ**
**ማልሁ፥ አጸናሁም።**
**107እጅግ ተቸገርሁ**
**አቤቱ፥ እንደ ቃልህ ሕያው አድርገኝ።**
**108አቤቱ፥ ከአፌ የሚወጣውን ቃል ውደድ፥**
**ፍርድህንም አስተምረኝ።**
**109ነፍሴ ሁልጊዜ በእጅህ ውስጥ ናት**
**ሕግህን ግን አልረሳሁም።**
**110ኃጢአተኞች ወጥመድን ዘረጉብኝ**
**ከትእዛዝህ ግን አልሳትሁም።**
**111የልቤ ደስታ ነውና**
**ምስክርህን ለዘላለም ወረስሁ።**
**112ለዘላለም ለፍጻሜውም**
**ትእዛዝህን አደርግ ዘንድ ልቤን አዘነበልሁ።**

**119፡105** እዚህ ቁጥር ላይ ግሥ የለም። የእግዚአብሔር ቃል ሕይወትን ያበራል (መዝ. 43:3፤ምሳ. 6:23፤2 ጴጥ. 1:19)። ሕይወት የተገለጸው እንደ መንገድ፣ በግልጽ እንደ ተመለከተ መንገድ ነው፣ በመለኮታዊ ራዕይ እንደተመለከተ (መዝ. 89:15፤ኢሳ. 2:5፤1 ዮሐንስ 1:7)። ወደ ቀኝም ወደ ግራም መዞር ጥፋትን ያመጣል።

ከአኪ እንደምንረዳው የእግዚአብሔር የመዳረሻ ራዕይ (ቃል) ኢየሱስ ነው (ዮሐንስ 1:1-14፤ፊሊ. 2:6-11፤ቆላ. 1:13-16፤ዕብ. 1:2-3)። እሱ የዓለም ብርሃን ነው (ዮሐንስ 1:4፤8:12፤9:5)።

**119፡106** መዝሙረኛው ያስረግጣል፣ በእግዚአብሔር ራዕይ መንገድ መራመዱን። የግሡ መልክ የሚያመለክተው መነሻ ውሳኔን እና ቀጣይነት ያለውን ለእግዚአብሔር ራዕይ መሰጠትን ነው። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት "በር" ነው (መነሻ፣ ከእግዚአብሔር ጋር በግል መገናኘ) እና "መንገድ/ፍኖት" (ቀጣይነት ያለው የሕይወት ስልት፣ የየቀኑ ታዛዥነት)። ኢየሱስ ይሄንን አስተምሯል፣ ማቴ. 7:13-14 ላይ። እሱም ውሳኔና ደቀ-መዛሙርትነት ነው።

በዘመናዊው የአይሁድ ሕይወት፣ ወጣቶች የዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ ያጠናሉ፣ እናም በ13 ዓመት ወንዶች እና በ12 ልጃገረዶች፣ እሱን ለመጠበቅ ቃል ይገባሉ (ራሳቸውን ይሰጣሉ) (ባር-ሚዝቫህ፣ ባት-ሚዝቫህ)።

**119፡107** የመከራው አፈጣጠር ርግጠኝነት የለውም። እሱም ሊሆን የሚችለው

1. ኃጢአተኞች፣ መዝ. 119:110 (ኢዮብ 24:13)
2. እግዚአብሔር ራሱ፣ ለመዝሙረኛው የቀድሞ አለመታዘዝ (መዝ. 119:67፣71)

▣ **"ሕያው አድርገኝ"** ይህ በጥሬው "ሕይወት ስጠኝ" ማለት ነው (ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309) እናም ተደጋጋሚ ጥያቄ ነው (መዝ. 119:25፣37፣40፣ 50፣88፣93፣107፣149፣154፣156፣159፣175)። እዚህጋ ሊል የሚችለው ሥጋዊ ሕይወትን ነው፣ ግን አንዱ የእግዚአብሔርን ራዕይ የሚያውቅ፣ እሱ ደግሞ ጤነኛ መንፈሳዊ ሕይወትን እንደሚገልጽ ያውቃል። ሕይወት የመጣው "እንደ ቃልህ ነው።"

**119:108ሀ** ይህ ቁጥርና እሱን የመሰሉ ሌሎች የአይሁድ ሕዝቦች ያህዌን በቃል የሚያመልኩበት መነሻ ነው፣ በመሥዋዕት ሳይሆን፣ መቅደሳቸው በመፍረሱ ምክንያት (ኢሳ. 57:19፤ሆሴዕ 14:2፤ዕብ. 13:15)።

**119:8ለ** መረዳት አይቻልም፣ ያለ መለኮት ርዳታ። እግዚአብሔር አእምሯችንን ወደ ራሱ መክፈት ይሻል፣ እና ወደ እሱ የሕይወት ምሪት (መዝ. 119:12፣26፣64፣66፣68፣124፣135፣171)።

**119:109 "ነፍስ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ኔፊሽ ነው (ቢ.ዲ.ቢ 659)። ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት ዘፍ. 35:18 ላይ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር።

▣ **"በእጅህ"** ይህንን የዕብራይስጥ ፈሊጥ በሁለት መንገዶች መረዳት ይቻላል።

1. በአሉታዊ መልኩ፣ "እጅ" አንዱ በሌላው ላይ ያለውን ኃይል ስለሚያሳይ (መሳ. 12:3፤1 ሳሙ. 19:5፤28:21፤ኢዮብ 13:14፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ)
2. በአዎንታዊ መልኩ፣ "እጅ" የእግዚአብሔርን የመጠበቂያ ኃይልና ከለላነቱን ስለሚያሳይ (ማለትም፣ መዝ. 31፡5)

ኤምቲ "በእጄ" የሚል ሲኖረው፣ LXX ደግሞ "በእጅህ" የሚል አለው። የመጀመሪያው የሚገልጸው፣ የእግዚአብሔርን ራዕይ (ቃል) መከተል ማለት ለወደቀው ዓለም ተቃዋሚ መሆን ነው። ሁለተኛው የሚገልጸው የእግዚአብሔርን የጥበቃ ኃይልና ክብካቤ ነው (አኢመቅ)።

**119:110** መዝሙረኛው በአንዳንድ የኪዳን ጥሰቶች ይከሰሳል፣ ነገር ግን እሱ ለእግዚአብሔር ራዕይ (ቃል) ያለውን ታማኝነት ያስረግጣል።

"ወጥመድ" እንደ "ጉድጓድ" መዝ. 119፡85 ላይ እንዳለው፣ የእንሰሳ ወጥመድ ነው፣ እዚህጋ በዘይቤነት ጥቅም ላይ የዋለው ለሰው የከፋ ጥቃት ነው።

**119:111-112** የእግዚአብሔር ራዕይ ለእስራኤል፣ ከእርሱ ጋር የተለየ ግንኙነት እንዳላቸው ማስረጃ ነበር። መዝሙረኛው ለዛ ራዕይ ታማኝነቱንና ታዛዥነቱን ያስረግጣል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ።

**119:111 "እርሱ የልቤ ደስታ ነውና"** እስራኤል በእግዚአብሔር ራዕይ ተደስቷል (መዝ. 1:2፤19:7-11)። እግዚአብሔርን ለሚያውቁት ለእነርሱ፣ ሸክም አይሆንባቸውም ደስታ እንጂ (መዝ. 119:14፣16፣24፣35፣47፣ 70፣77፣92፣143፣162፣174)።

**119:112 "ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም ('ኦላም)።

▣ **"ለፍጻሜውም"** ተመሳሳይ የሆነ ቀጣይነት ያለውን የቁርጠኝነት ገለጻ ተመልከት (መዝ. 119፡106) ለእግዚአብሔር ራዕይ፣ መዝ. 119፡33።

**መዝሙር ፡119፡113-120 (ሳምኬት)**

**113 ዓመፀኞችን ጠላሁ፥**
**ሕግህን ግን ወደድሁ።**
**114 አንተ ረዳቴና መጠጊያዬ ነህ፥**
**በቃልህም ተማመንሁ።**
**115 እናንተ ኃጢአተኞች፥ ከእኔ ራቁ፥**
**የአምላኬንም ትእዛዝ ልፈልግ።**
**116 እንደ ቃልህ ደግፈኝ፥ ሕያውም እሆናለሁ።**
**ከተስፋዬም አልፈር።**
**117 እርዳኝ እድናለሁም፥**
**ሁልጊዜም ሥርዓትህን እመረምራለሁ።**
**118 ምኞታቸው ዓመፃ ነውና**
**ከሥርዓትህ የሚርቁትን ሁሉ አጐሳቈልሃቸው።**
**119 የምድርን ኃጢአተኞች ሁሉ እንደ ርኵሰት አጠፋሃቸው**
**ስለዚህ ምስክርህን ወደድሁ።**
**120 ሥጋዬ አንተን ከመፍራት የተነሣ ደንገጠ**
**ከፍርድህ የተነሣ ፈርቻለሁ።**

**119:113 "ዓመጸኞችን ጠላሁ"** ቅጽሉ "ልበ-መንታ" (ቢ.ዲ.ቢ 704 II) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው። ጀፒኤስኦኤ እሱን የሚተረጉመው "ልቡ የተከፈለ" በሚል ነው። እሱም ከስሙ ጋር ይዛመዳል (ቢ.ዲ.ቢ 704) 1 ነገ. 18:21 ላይ ከሚገኘው። ያዕቆብ 1:8፤4:8 ተመልከት።

ይህ አንጓ ሁለት ዓይነት ግለሰቦችን ያነጻጽራል።

1. የመዝሙረኛው አሳዳጆች
   - ሀ. ሁለት ሐሳብ ያላቸው፣ መዝ. 119:113ሀ
   - ለ. ከፉ አድራጊዎች፣ መዝ. 119:115
   - ሐ. ከእግዚአብሔር ሥርዓት የሚርቁ፣ መዝ. 119:118ሀ
   - መ. ዓመጸኞች፣ መዝ. 119:118ለ
   - ሠ. ኃጢአተኞች፣ መዝ. 119:119
2. መዝሙረኛው
   - ሀ. የእግዚአብሔርን ሕግ ይወድዳል፣ መዝ. 119:113ለ
   - ለ. የእግዚአብሔርን ቃል ይጠብቃል፣ መዝ. 119:114ለ

ሐ. የእግዚአብሔርን ተእዛዛት ይፈልጋል፣ መዝ. 119:115ለ
መ. የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይመረምራል፣ መዝ. 119:117ለ
ሠ. የእግዚአብሔርን ምስክርነቶች ይወድዳል፣ መዝ. 119:119ለ
ረ. የእግዚአብሔርን ፍርድ ይፈራል፣ መዝ. 119:120ለ

▣ **"እወድዳለሁ"** ግልጽ የሆነው ተቃርኖ ሰፊውን የዳበረ ክፍተት ያሳያል፣ እግዚአብሔርንና የእርሱን ራዕይ በሚወዱትና በማይወድዱት መካከል ያለውን! ገለልተኛ ስፍራ የለም።

**119:114 "እግዚአብሔር መጠጊያዬ ነው"** ስሙ (ቢዲቢ 712) መጠጊያን ይገልጻል።
1. ማደሪያ ድንኳን/መቅደስ – መዝ. 27:5
2. እግዚአብሔር ራሱ – መዝ. 31:20፤32:7፣10
3. የክንፎቹ መጠጊያ – መዝ. 61:5
4. የሁሉን ቻዩ (እግዚአብሔር) ጥላ – መዝ. 91:1 (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጥላ እንደ ዘይቤ ለመጠጊያና ለክብካቤ)

▣ **"ጋሻዬ"** ስሙ (ቢዲቢ 171) ሰውኛ ዘይቤ ሆኗል፣ እግዚአብሔር ለተከታዮቹ ጠባቂ ለመሆኑ።
1. አብርሃም – ዘፍ. 15:1
2. እስራኤል – ዘዳ. 33:29፤መዝ. 33:20፤59:11፤115:9፣10
3. መዝሙረኛው – መዝ. 3:3፤18:2፤28:7፤84:9
4. ጻድቅ ሰው – መዝ. 5:12
5. ልበ ቅን – መዝ. 7:10
6. እሱን የሚጠጉ – መዝ. 18:30፣35፤ምሳ. 30:5
7. በቅንነት የሚራመዱ – መዝ. 84:11፤ምሳ. 2:7
8. የሚፈሩት – መዝ. 115:11
9. ንጉሡ – መዝ. 144:2

▣ **"በቃልህም ተማመንሁ።"** ግሡ (ቢዲቢ 403፣ ኬቢ 407፣ ፒኤል የተጠናቀቀ) የሚገልጸው ተስፋንና ትዕግሥት ያለበትን መታመን ነው፣ እግዚአብሔር ተስፋውን እንዲፈጽም (መዝ. 31:24፤33:18፣22፤69:3፤119:43፣49፣74፣81፣114፣147)።

**119:115-117** እነዚህ የቅኔ ስንኞች ሁሉ የሚጀምሩት በተተኳሪ ነው (ማለትም፣ የጸሎት ጥያቄ)። ሁሉም ሥሮች የሚጀምሩት በሳምኬት ነው።
1. ክፉ አድራጊዎች ከእኔ ራቁ – ቢዲቢ 693፣ ኬቢ 747፣ ቃል ተተኳሪ
2. እንደ ቃልህ ዕርዳኝ – ቢዲቢ 701፣ ኬቢ 759፣ ቃል ተተኳሪ
3. ደግፈኝ – ቢዲቢ 703፣ ኬቢ 761፣ ቃል ተተኳሪ

ሁለተኛው ስንኝ የመሻትን ውጤት እንዴት እንደሚሰጥ ተመልከት።
1. ትእዛዛትህን እፈልግ ዘንድ – ቃል ተጓዳኝ
2. በሕይወት እኖር ዘንድ – ቃል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. እድን ዘንድ – ኒፋል ተጓዳኝ (መዝ. 119:117ሀ)
4. ሥርዓትህን እመረምር ዘንድ (መዝ. 119:117ለ)

**119:118** ይህ ቁጥር ለጣዖት አምላኪነት ፍንጭ ይሰጣል (ኢሳ. 28:15፤ኤር. 10:14፤51:17)፣ ለኪዳን አለመታዘዝ ሳይሆን።

"አለመቀበል" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 699፣ ኬቢ 756) እዚህ ብቻ እና ሰቆ. 1:15 ላይ ነው የሚገኘው። ይህ ሌላው ምሳሌ ነው፣ ካልተወዘተሩ ቃላት መስቀልያውን መልክ ለመግጠም የተመረጠው።

**119፡119-120** "ፍቅር" (ዘዳ. 6:4-6) እና "ፍርሃት" (መዝ. 119:120) አንድ ላይ መሄዳቸውን ተገንዘብ። ለዩኒቨርስ ፈጣሪ የሚገባው ክብር አለ (ማለትም፣ ኒዶቲ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 529)፣ እሱም ደግሞ የዩኒቨርስ አዳኝ የሆነ፣ እሱም ደግሞ የዩኒቨርስ ፈራጅ የሆነ!

"መንቀጥቀጥ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 702፣ ኬቢ 760፣ ቃል የተጠናቀቀ) እዚህ ጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ እንዲሁም ፒኤል ኢዮብ 4፡15 ላይ ብቻ ነው የሚገኘው። ተዛማጅ መልክ (ማለትም፣ የተለዩ አናባቢዎች) ኤር. 51፡27 ላይ ብቻ ነው የሚገኘው። ይህም ሌላው የማይዘወተር ቃል ነው፣ መስቀልያ መልኩን ለመግጠም ጥቅም ላይ የዋለ።

**119:119**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ኃጢአተኞችን አጠፋሃቸው"** |
| **አኪጀቅ** | **"ኃጢአተኞችን ሁሉ አስወገድካቸው"** |
| **አየተመቅ** | **"ኃጢአተኞችን ሁሉ. . .እንደ ርኩሰት ቆጠርካቸው"** |
| **አኢመቅ** | **"በዓይህ ፊት ኃጢአተኞች ሁሉ. . .እንደ ዝገት ናቸው"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ኃጢአተኞችን አስወገድካቸው"** |
| **LXX** | **"ኃጢአተኞች ሁሉ. . .እንደ ሕግን ተላላፊ እቆጥራቸዋለሁ"** |

ቢዲቢ 991 እና ኬቢ 1409 በርካታ ሐሳብ አላቸው፣ ለዚህ ሥር ሂፊል።
1. ዝም ማሰኘት፣ ወደ ፍጻሜ ማምጣት፣ መዝ. 46:9
2. ማጥፋት፣ መደምሰስ፣ መዝ.8:2፤19:119
3. የመታቀብ መልክ ማስያዝ
4. ማስወገድ፣ መዝ. 89፡44
5. እንዳይሳካ ማድረግ

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 411) ሁለት አማራጮች አሉት።
1. እንዲያቆሙ አደረግካቸው
2. ተገነዘብክ/ተገንዝበሃል
እሱም "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል (ምክንያታዊ ጥርጣሬ) ለ ቁ. 2።
የመጀመሪያው ቃል የመዝ. 119፥119 "ርኩሰት" ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 691)፣ እሱም ከተለመደው አገባብ ውጭ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መስቀልያ ፈርጁን ለመግጠም። እሱ የሚጠቅሰው ተረፈ-ምርትን (ቆሻሻ) ነው፣ ብረት ከማቅለጥ። እሱም ጥቅም የሌለውና የሚጣል ነው።

## መዝሙር ፥119፥121-128 (ዔ)

**121ፍርድንና ጽድቅን ሠራሁ**
**ለሚያስጨንቁኝ አሳልፈህ አትስጠኝ።**
**122ባሪያህን በመልካም ጠብቀው**
**ትዕቢተኞችም አይጋፉኝ።**
**123ዓይኖቼ ለማዳንህ፥**
**ለጽድቅህም ቃል ፈዘዙ።**
**124ለባሪያህ እንደ ምሕረትህ አድርግ፥**
**ሥርዓትህንም አስተምረኝ።**
**125እኔ ባሪያህ ነኝ እንዳስተውል አድርገኝ፥**
**ምስክርህንም አውቃለሁ።**
**126ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ ነው፥**
**ሕግህንም ሻሩት።**
**127ስለዚህ ከወርቅና ከዕንቍ ይልቅ**
**ትእዛዝህን ወደድሁ።**
**128ስለዚህ ወደ ትእዛዝህ ሁሉ አቀናሁ፥**
**የዓመፅንም መንገድ ሁሉ ጠላሁ።**

**119፥121-128** ይህ አንጓ የተለመደውን ፈርጅ ይከተላል። መዝሙረኛው ራሱን ይገልጻል፣ ከሚቃወሙት ጋር በማቃረን።
1. መዝሙረኛው
   ሀ. ፍርድን አድርጓል (ቢ.ዲ.ቢ. 1048)፣ መዝ. 119:121
   ለ. ጽድቅን አድርጓል (ቢ.ዲ.ቢ. 841)፣ መዝ. 119:121
   ሐ. ዓይኖቹ የእግዚአብሔርን ማዳን ከመናፈቅ ፈዝዘዋል፣ መዝ. 119:123ሀ
   መ. ዓይኖቹ የእግዚአብሔርን የጽድቅ ቃል ከመናፈቅ ፈዝዘዋል፣ መዝ. 119:123ለ
   ሠ. እሱ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው መዝ. 119:122፣124፣125
   ረ. እሱ የእግዚአብሔርን ትእዛዛት ይወድዳል፣ መዝ. 119:127
   ሰ. እሱ በእግዚአብሔር ራዕይ ሁሉ ይደሰታል፣ መዝ. 119:128ሀ
   ሸ. እሱ የሐሰትን መንገድ ሁሉ ጠልቷል፣ መዝ. 119:128ለ (መዝ. 31:6፤119:104፣163፤ምሳ. 13:5)
2. የእርሱ ጠላቶች ባሕርያቸው
   ሀ. የሚጨቁኑኝ (ቢ.ዲ.ቢ. 798፣ ኬቢ. 897፣ ቃል አንቀጽ)፣ መዝ. 119:121ለ
   ለ. ትዕቢተኞች፣ መዝ. 119:122ለ (መዝ. 119:21፣51፣69፣78፣85)
   ሐ. የእግዚአብሔርን ሕግ ሽረዋል፣ መዝ. 119:126ለ
   መ. የሐሰትን መንገድ ይወድዳሉ (በአንድምታ)፣ መዝ. 119:128ለ

**119፥121 "ፍርድ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፈራጅ፣ ፍርድ፣ እና ፍትሕ።

▣ **"ጽድቅ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ።

**119፥122** ይህ ከአምስቱ የጸሎት ጥያቄዎች የመጀመሪያው ነው።
1. ለባርያህ ዋስትና መልካም አድርግ፣ መዝ. 119:122ሀ – ቢ.ዲ.ቢ. 786፣ ኬቢ. 876፣ ቃል ተተኳሪ ("ቃልህን ስጥ")፣ ኢዮብ 17:3፤ኢሳ. 38:14
2. ለትዕቢተኛም አትፍቀድ (ቢ.ዲ.ቢ. 267) ይቃወመኝ ዘንድ፣ መዝ. 119:122ለ – ቢ.ዲ.ቢ. 798፣ ኬቢ. 897፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ። ቃል የድርጊት አንቀጽ መዝ. 119:121 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል የጠላቶቹን ባሕርይ ለመሳል (ለማሳየት)።
3. ለባርያህ እንደ ምሕረትህ አድርግ፣ መዝ. 119:124ሀ – ቢ.ዲ.ቢ. 793፣ ኬቢ. 889፣ ቃል ተተኳሪ። የያህዌ ሄሰድ (ቢ.ዲ.ቢ. 338) ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ መዝ. 51:1፤106:45፤109:26፤119:88፣149፣159.
4. ሥርዓትህን አስተምረኝ፣ መዝ. 119:124ለ – ቢ.ዲ.ቢ. 540፣ ኬቢ. 531፣ ፒል ተተኳሪ፣ ይህም ሌላው ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ መዝ. 119:12፣26፣64፣108፣135፣171
5. ማስተዋልን ስጠኝ፣ መዝ. 119:125ሀ – ቢ.ዲ.ቢ. 106፣ ኬቢ. 122፣ ሂፊል ተተኳሪ፣ ይህም ሌላው ተደጋጋሚ ጭብጥ ነው፣ ኢዮብ 32:8፤ መዝ. 119:27፣34፣73፣125፣130፣144፣169

**"በመልካም"** ዳሆድ ልክ ሊሆን ይችላል (ኤቢ. ተመልከት፣ ቅጽ 17ሀ፣ ገጽ 187) ማለትም ከ "መልካም" በፊት ላሜድ (ቢ.ዲ.ቢ. 373 II) የስም ጠቃሹን ይገልጽ ይሆናል (ማለትም፣ መልካሙ ሆይ)፣ መዝ. 119:126 ላይ እንዳደረገው፣ ከያህዌ ፊት፣ "ጌታ ሆይ" በሚል የተተረጎመው።

▣ አአመመቅ የጥናት መጽሐፍ ቅዱስ (ገጽ 869) አስደናቂ አስተውሎትን ያደርጋል፣ የአይሁድን ማሶራ ማስታወሻ ተከትሎ፣ ማለትም መዝ. 119፡122 ብቸኛው ቁጥር ነው መዝሙር 119 ላይ፣ ቀጥተኛ ወይም ቀጥተኛ ያልሆነ (ማለትም፣ መዝ. 119:90፤121፤132) ማጣቀሻ ለእግዚአብሔር ራዕይ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ) አይከሰትም። ሆኖም፣ ዳሆድ ኤቢ ላይ (ገጽ 193) ያስረግጣል 119:37፤90፤121፤122፤132፣ እና 149 የተለየ ቃል ለእግዚአብሔር ራዕይ እንደሌላቸው።

**119፡123** ደኅንነት ዘወትር አካላዊ ትድግናን ይጠቅሳል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት [ብኪ]) እዚህ ግን ቀጣዩ ስንኝ የሚያመለክተው ሁሉም የእግዚአብሔር የተስፋ ቃሎች ወደ ፍሬአማነት እንዲመጡ መናፈቅን ነው (አንድምታውም ብሔራዊ እና ይልቁንም የፍጻሜ ዘመናዊ ተስፋዎች)።

**119፡124 "ምሕረት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት (*ሄሰድ*)።

**119፡125 "እውቅ ዘንድ"** እዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ላይ "ማወቅ" (ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ *ቃል ተጓዳኝ*) በርግጠኝነት የሚጠቅሰው የተጠቃለለ እውቀትን ነው። ሆኖም፣ የዕብራይስጡ ግሥ ዘወትር የሚያመለክተው የግላዊ ግንኙነትን ይዘት ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ።

**119፡126 "ለእግዚአብሔር የሥራ ጊዜ ነው፥"** ታማኝ ተከታዮች የእግዚአብሔርን ቃልና ተስፋዎች ከምር ይወስዳሉ። እነርሱ ከፉውንና በፍጥረት ያለውን ሁከት ይመለከቱና እግዚአብሔር በሰዎች ታሪክ ውስጥ ጣልቃ ገብቶ ቃሉን ሁሉ እንዲፈጽም በናፍቆት ይሻሉ (ሮሜ. 8፡18-25)!

**119፡127ለ** ይህ መዝ. 19:10ን ያስታውሰኛል (መዝ. 119:103)! እንዴት ድንቅ ነው፣ እግዚአብሔር በራዕዩ በኩል ራሱን ሲገልጥ። እሱ አማኞችን ተስፋ ቢስ አድርጎ አልተዋቸውም፣ በዚህ በወደቀ ዓለም/ዘመን ስፍራና ጊዜ ውስጥ። እሱ ፍቃዱንና መንገዱን አስታውቆናል፣ ከእርሱ ጋር አሁን የቅርብ ወዳጅነት ይኖረን ዘንድ!

**119፡128** ይህ የታማኝ ተከታዮች ርዕዮተ-ዓለም ነው። አማኞች በርግጥ የእግዚአብሔርን ራዕይ ሁሉ መረዳት አይችሉም፣ ግን በእግዚአብሔር ይታመናሉ። ይህም በትክክል ተቃራኒው ነው፣ ከእነዚያ ጋር

1. አንዳንዶቹን ራዕዮች ከመረጡት ጋር፣ ሁሉንም ሳይሆን (መዝ. 119፡113)
2. ሌሎች አማልክትን ከመረጡት ጋር (ማለትም፣ ጣዖት አምላኪነት፣ መዝ. 31:6፤119:104፤ኤር. 10:3)

በርካታ ጥያቄዎች አሉ፣ በመዝ. 119፡128 ላይ።

1. ለምን "ስለዚህ" በሚል ጀመረ፣ ይህ ከሎጂካዊነት አኳያ ከመዝ. 119፡127 ጋር የማይያያዝ ሆኖ ሳለ? ከመስቀልያው (ቅኔ) ጋር ጋር እንዲገጥም ለማድረግ ሊሆን ይችላል (119፡127 ደግሞ "ስለዚህ" በማለት ይጀምራል፣ ለመስቀልያ ዓላማ)።
2. "ሁሉም" የሚለው ለምን ተደጋግሞ ጥቅም ላይ ዋለ?
3. ግሡ ኀሠን ለምን ሆነ (ቢዲቢ 448፣ ኬቢ 449፣ ፒኤል የተጠናቀቀ)፣ እሱም ዘወትር "ለስላሳ መሆን፣" "ቀና መሆን፣" ወይም "ቀጥተኛ መሆን" በሚል የሚተረጎም። እሱ ምናልባት እውነተኛውን መንገድ/ፍኖት የሚገልጽ ይሆናል (ማለትም፣ "ጽድቅ" እንደ መስፈሪያ (መለኪያ) ዘንግ/ሸንበቆ፣ ምሳ. 3፡6) አልያም (በተቃርኖ) "የሐሰት ፍኖት/መንገድ።"

**መዝሙር ፡119፡129-136 (ፌ)**

**[129]ምስክሮችህ ድንቆች ናቸው**
**ስለዚህ ነፍሴ ፈለገቻቸው።**
**[130]የቃልህ ፍቺ ያበራል፥**
**ሕፃናትንም አስተዋዮች ያደርጋል።**
**[131]አፌን ከፈትሁ፥ አለከለከሁም**
**ወደ ትእዛዝህ ናፍቄአለሁና።**
**[132]ስምህን ለሚወድዱ እንድምታደርገው ፍርድ፥**
**ወደ እኔ ተመልከተ ማረኝም።**
**[133]አካሄድን እንደ ቃልህ አቅና**
**ኃጢአትም ሁሉ አይግዛኝ።**
**[134]ከሰው ግፍ አድነኝ**
**ትእዛዝህንም እጠብቃለሁ።**
**[135]በባሪያህ ላይ ፊትህን አብራ፥**
**ሥርዓትህንም አስተምረኝ።**
**[136]ሕግህን አልጠበቅሁምና**
**የውኃ ፈሳሽ ከዓይኖቼ ፈሰሰ።**

**119፡129 "ድንቆች"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተአምራት።

▣ **"ነፍስ"** ይህ *ኔፌሽ* ነው (ቢዲቢ 659)፣ እሱም የሰውን ሕይወት የሚገልጽ። ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት ዘፍ. 35፡18 ላይ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር።

▣ **"ፈለገቻቸው"** ይህ ተደጋጋሚ አጽንዖት ነው (መዝ. 119:2፤22፤33፤34፤56፤69፤100፤115፤129፤145፤168፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ)። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ብርሃን ብቻ አይደለም፣ ግን ብብርሃን መጓዝ እንጂ (መዝ. 89:15፤119:105፤ምሳ. 6:23፤ኢሳ. 2:5፤1 ዮሐንስ 1:5-7)። ተመሳሳይ የሆነ አጽንዖት ስለ መታዘዝ መዝ. 119፡134ለ ላይ ተመልከት፣ "ማወቅ" *ቃል ተጓዳኝ* (ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581)።

**119:130 "የማይታጠፍ"** ይህ የቃሉ ብቸኛ አጠቃቀም ነው (ቢዲቢ 636) ብኪ ላይ። እንደገና ያልተለመደ ቃል ጥቅም ላይ ውሏል፣ የመስቀልያውን መልክ (ቅኔ) ለመግጠም።

▣ **"ሕፃናት"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 834) አሉታዊ (ማለትም፣ ምሳ. 1:22) ወይም አዎንታዊ ፍች ሊኖረው ይችላል። እዚህ ጋ አዎንታዊ ነው። እግዚአብሔር ሰዎች ሁሉ እርሱንና ፍቃዱን እንዲያውቁ ይሻል። እዚህጋ የሚገልጸው ለመማር ዝግጁ የሆነ ሰውን ነው (መዝ. 19:7) ግን አንዱ በማንኛውም ምክንያት፣ የእግዚአብሔርን ራዕይ (ቃል) የማያውቅ።

**119:131** እነዚህ ሦስት ፈሊጦች ናቸው ለብርቱ መሻት።

1. አፍን መከፈት – ኢዮብ 29:23
2. ማለክለክ – መዝ. 42:1
3. መናፈቅ – ምሳ. 119:20

የመጨረሻው ቃል (ቢዲቢ 383) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ።

**119:132-135** ተከታታይ ተተኳሪአዊ የጸሎት ጥያቄዎች አሉ።

1. ወደ እና ዞር – ቢዲቢ 815፣ ኬቢ 937፣ *ቃል ተተኳሪ*፣ መዝ. 25:16፤69:16
2. ማረኝም – ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334፣ *ቃል ተተኳሪ*
3. አካሄዴን አቅና – ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 464፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
4. አድነኝ – ቢዲቢ 804፣ ኬቢ 911፣ *ቃል ተተኳሪ* (ልዩ ርዕስ ተመልከት: መዋጀት/መቤዠት)
5. በባሪያህ ላይ ፊትህን አብራ – ቢዲቢ 21፣ ኬቢ 24፣ *ሂፊልተተኳሪ*
6. አስተምረኝ – ቢዲቢ 540፣ ኬቢ 531፣ *ፒል ተተኳሪ*

አንድ ተጨማሪ ጥያቄ አለ፣ በአሉታዊ የተቀመጠ (ማለትም፣ "ማንም በእኔ ላይ አይግዛ፣" መዝ. 19:13፣ ግን በተለየ ግሥ)። እሱ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ ነው በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 119:133ለ።

**119:132ለ** እንዴት ያለው የተዋበ ባሕርይ ነው፣ የእግዚአብሔር ታማኝ ተከታዮች (መዝ. 5:11፤69:36፤ኢሳ. 56:6)!

ስሙ እግዚአብሔርን ራሱን ይወክላል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ።

**119:133 "አካሄዴን አጽና"** ይህ ግልጽ የሆነ፣ የምቹ፣ እንቅፋት የሌለበት መንገድ ምናባዊ ምስያ ነው (መዝ. 17:5)፣ ይኸውም በእግዚአብሔር ራዕይ፣ ሥራ፣ እና ተስፋ ቃል እውን ሊሆን የሚችል (ማለትም፣ ኢሳ. 40:3-4)።

**119:135 "በባሪያህ ላይ ፊትህን አብራ፥"** ይህ ጠቃሽ ነው፣ ለአሮናዊ ባርኮት፣ ዘኍ. 6:24-26። እሱም በርካታ ጊዜ መዝሙር ላይ ተጠቅሷል (መዝ. 4:6፤31:16፤67:1፤80:3፣7፣19፣ እና እዚህጋ)።

ተቃራኒው ፈሊጥ የሚሆነው ያህዌ ፊቱን ሲደብቅ ነው (መዝ. 10:11፤13:1፤22:24፤27:9፤44:24፤69:17፤88:15፤102:2፤104:29፤143:7፤ኢሳ. 57:17)።

**119:136** ይህ ጠቃሚ ቁጥር ነው፣ ምክንያቱም የአብዛኞቹ የእግዚአብሔርን ሕግ የማይጠብቁት ተጠቃሾች ፍርድን ስለሚያመለክት (ማለትም፣ መዝ. 119:53፣158)። ይኸኛው የሚያሳየው የመዝሙረኛውን ኀዘንና ምልጃ ነው፣ ለመውጫ መንገድ።

አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ መዝሙረኛው የሚያስበው ስለ ግል ጠላቶቹ ወይም ስለ እስራኤል የተጠቃለለ ኃጢአት ለመሆኑ (ኤር. 9:1፣18፤14:17፤ሰቆ. 3:48)።

## መዝሙር :119:137-144 (ጻዴ)

**137 አቤቱ፥ አንተ ጻድቅ ነህ፥**
**ፍርድህም ቅን ነው።**
**138 ምስክርህን በጽድቅ አዘዝህ፥**
**እጅግም ቅን ነው።**
**139 ጠላቶቼ ቃልህን ረስተዋልና**
**የቤትህ ቅንዓት አቀለጠኝ።**
**140 ቃልህ እጅግ የነጠረ ነው፥**
**ባሪያህም ወደደው።**
**141 እኔ ታናሽና የተናቅሁ ነኝ**
**ትእዛዛትህን ግን አልረሳሁም።**
**142 ጽድቅህ የዘላለም ጽድቅ ነው፥**
**ቃልህም እውነት ነው።**
**143 መከራና ችግር አገኙኝ**
**ትእዛዛትህ ግን ተድላዬ ናቸው።**
**144 ምስክርህ ለዘላለም ጽድቅ ነው**
**እንዳስተውል አድርገኝ፥ በሕይወትም አኑረኝ።**

**119:137-144** ይህ አንጓ የሚያነጻጽረው የያህዌን እና የራዕዩን (የቃሉን) የነጠረ መሆንና መዝሙረኛው ያለበትን ወቅታዊ ሁኔታ ነው።

1. ያህዌ/የእርሱ ራዕይ ባሕርዩ
   ሀ. ጻድቅ
      (1) ቅጽል (ቢ.ዲ.ቢ. 843)፣ መዝ. 119:137
      (2) ስም (ተባዕታይ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 841)፣ መዝ. 119:138፣144 (አንስታይ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 842፣ መዝ. 119:142)
   ለ. መልካም (ቢ.ዲ.ቢ. 449)፣ መዝ. 119:137
   ሐ. ታማኝ (ADVERB፣ ቢ.ዲ.ቢ. 547)፣ መዝ. 119:138፣ መዝ. 119:86
   መ. ንጹሕ(ቢ.ዲ.ቢ. 864፣ ኬቢ. 1057፣ ቃል ተገብሮ አንቀጽ)፣ መዝ. 119:140
   ሠ. ዘላለማዊ (ቢ.ዲ.ቢ. 761)፣ መዝ. 119:142፣144
   ረ. እውነት (ቢ.ዲ.ቢ. 54)፣ መዝ. 119:142
2. መዝሙረኛው
   ሀ. ለእግዚአብሔር ራዕይ ቅንዓት አለው (ወይም በጠላቶቹ ላይ) ነገር ግን ጠላቶቹ ረስተዋቸዋል፣ መዝ. 119፡139
   ለ. የእግዚአብሔርን ራዕይ ይወድዳል፣ መዝ. 119፡140
   ሐ. እሱ ታናሽና የተናቀ ነው ነገር ግን የእግዚአብሔርን ራዕይ አልረሳም፣ መዝ. 119፡141
   መ. ችግርና ኀዘን በእርሱ ላይ ቢመጣበትም፣ በእግዚአብሔር ራዕይ ተደስቷል፣ መዝ. 119፡143

**119፡137 "ጼታ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

**119፡139** ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ሊሆን የሚችለው የመዝሙረኛው "ቅንዓት" (ቢ.ዲ.ቢ. 888) የተመለከተው በአዎንታዊ አይደለም፣ ለእግዚአብሔር ቃል፣ ነገር ግን የእርሱን (የእግዚአብሔርን) ቃል በረሱት በእነርሱ ላይ እንጂ (መዝ. 69:9፤119:53)። ይህም የመዝ. 119:136 ተቃራኒ ነው።

**119:140**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀቅ** | **"እጅግ ንጹሕ"** |
| **አየተመቅ፣ LXX** | **"እጅግ የተፈተነ"** |
| **አእቅ** | **"ርግጠኛ"** |
| **አኢመቅ፣ የተእመቅ** | **"እጅግ የተፈተነ"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"እጅግ የነጠረ"** |

ግሡ (ቢ.ዲ.ቢ. 864፣ ኬቢ. 1057፣ ቃል ተገብሮ አንቀጽ) የሚገልጸው በእሳት የነጠረውን እና ቆሻሻው ከንጹሑ ብረት ላይ የተወገደውን ነው።

**119:141**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣ አየተመቅ፣ ፔሺታ** | **"ታናሽ"** |
| **አእቅ** | **"የማይጠቅም"** |
| **አኢመቅ** | **"ደካማ"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ጥቅመ- ቢስ"** |
| **LXX** | **"ታዳጊ"** |
| **የተእመቅ** | **"ታናሽ ጥቅም ያለው"** |

ጥያቄ የሚሆነው፣ ቃሉ የሚገልጸው (ቢ.ዲ.ቢ. 859 I)
1. ዕድሜን (ዘፍ. 43:33፤48:14፤መሳ. 6:15፤መዝ. 68:27)
2. አካላዊ መጠን (1 ሳሙ. 9:21፤ኢሳ. 60:22፤ኤር. 48:4፤49:20፤50:45)
3. ማኅበራዊ ዝና (አቋም) (ሚክያስ 5:2፤እና እዚህ)

▣ ይህ የጥንት ምሳሌ ነው ለብኪ. የተገላቢጦሽ ሚና። ታማኙ መዝሙረኛ "የተናቀ" በሚል ተጠርቷል (ቢ.ዲ.ቢ. 102፣ ኬቢ. 117፣ ኒፋል አንቀጽ) የእግዚአብሔርን ራዕይ ሆን ብለው የረሱት/የተዉት መሆን ሲገባቸው። ውጫዊ ሁኔታዎች (መዝ. 119:143) በዚህ በወደቀ ዓለም የእግዚአብሔርን ግምገማ አያንጸባርቁም፣ እሱም አንድ ቀን መዝገቡን በቀጥታ የሚያቀርበውን!

**119፡142 "እውነት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ ታማኝነት በብኪ።

**119፡143** ይህ ጻድቅ ለምን መከራ እንደሚቀበል ምሥጢር ነው (ኢዮብ፤ መዝሙር 73)። መዝሙረኛው የእግዚአብሔርን ራዕይ ይጠብቃል፣ ይወድዳል፣ እና ያደርጋል ነገር ግን አሁንም ገና መከራ ይቀበላል፣ ከክፉ ሰዎችና ከወደቀው ዓለም ሁኔታ (ማለትም፣ ሕመም፣ ማኅበራዊ ፍትሕ-አልባነት፣ ወዘተ)።

ችግሩ እግዚአብሔር ወይም ቃሉ አይደለም፣ ነገር ግን የፍጥረት የውድቀት ሁኔታ እንጂ (ዘፍ. 3:6፣11-12፣13፤መዝ. 14:3፤ሮሜ. 1:18-3:31)።

**119:144** ብቸኛው ተተኳሪአዊ የጸሎት ጥያቄ በዚህ አንጓ ላይ መዝ. 119:144ለ ነው (ዝከ. 119:27፣125)። መረዳት በመልካም አኗኗር ውጤቱ መታየት እንደሚኖርበት ተመልከት (ቢ.ዲ.ቢ. 310፣ ኬቢ. 309፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ)።

**መዝሙር ፡119፡145-152 (ቆፍ)**

**[145]በፍጹም ልቤ ጮኽሁ፥**
**አቤቱ፥ ስማኝ ሥርዓትህን እፈልጋለሁ።**

> [146]ወደ አንተ ጮኽሁ አድነኝ፥
> ምስክርህንም እጠብቃለሁ።
> [147]ማለዳ ጮኽሁ
> ቃልህንም ተስፋ አድርጌአለሁ።
> [148]ቃልህን አስብ ዘንድ
> ዓይኖቼ ለመማለድ ቀደሙ።
> [149]አቤቱ፥ እንደ ቸርነትህ ድምፄን ስማ
> እንደ ፍርድህ ሕያው አድርገኝ።
> [150]በዓመፃ የሚያሳድዱኝ ቀረቡ፥
> ከሕግህም ራቁ።
> [151]አቤቱ፥ አንተ ቅርብ ነህ፥
> መንገዶችህም ሁሉ ቅኖች ናቸው።
> [152]ከዘላለም እንደ መሠረትኸው
> ከቀድሞ ጀምሮ ከምስክርህ የተነሣ አወቅሁ።

**119፡145-152** በእነዚህ መስቀልያ (ቅኔ) አንጓዎች እንደ ተለመደው ሁሉ፣ መዝሙረኛው ድርጊቶቹንና ሐሳቡን ከአሳዳጆቹ ጋር ያነጻጽራል።

1. *መዝሙረኛው*
   *ሀ*. በፍጹም ልቤ ጮኽኩ፣ *መዝ*. 119:145*ሀ*
   *ለ*. *ሥርዓትህን እፈልጋለሁ*፣ *መዝ*. 119:145*ለ*
   *ሐ*. ወደ አንተ ጮኽኩ፣ *መዝ*. 119:146*ሀ*
   *መ*. ምስክሮችህን እጠብቃለሁ፣ *መዝ*. 119:146*ለ*
   *ሠ*. በማለዳ ተነሥቼ ለዕርዳታ ጮኽኩ፣ *መዝ*. 119:147*ሀ*
   *ረ*. *ቃልህን ጠበቅሁ*፣ *መዝ*. 119:147*ለ*
   *ሰ*. *ቃልህን አሰላስል ዘንድ*፣ *መዝ*. 119:148*ለ*
   *ሸ*. ከቀድሞ ጀምሮ ከምስክርህ የተነሣ አወቅሁ፣ *መዝ*. 119:152*ሀ*
2. ጨቋኞቹ
   *ሀ*. በዓመጻ የሚያሳድዱት ቀርበዋል፣ *መዝ*. 119:150*ሀ*
   *ለ*. እነርሱ ከሕግህ ርቀዋል፣ *መዝ*. 119:150*ለ*

▣ ከንጽጽሩ አኳያ መዝሙረኛው አራት የጸሎት ጥያቄዎችን ያቀርባል።
1. ስማኝ፣ *መዝ*. 119:145*ሀ* – ቢዲቢ 772፣ ኬቢ 851፣ *ቃል ተተኳሪ*
2. አድነኝ፣ *መዝ*. 119:146*ሀ* – ቢዲቢ 446፣ ኬቢ 448፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
3. ድምጼን ስማ፣ *መዝ*. 119:149*ሀ* – ቢዲቢ 1033፣ ኬቢ 1570፣ *ቃል ተተኳሪ*
4. ሕያው አድርገኝ፣ *መዝ*. 119:149*ለ* – ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ *ፒል ተተኳሪ*

ይህ ተጨማሪ ታሳቢ ጥያቄ ነው *መዝ*. 119:151*ሀ* ላይ። ኃጢአተኞች ወደ እርሱ እንደቀረቡ፣ እሱም ያስረግጣል፣ ያህዌ ቅርብ መሆኑን፣ *መዝ*. 119:151። እሱ ዓረፍተ-ነገር ነው (ግሥ የሌለው)፣ ግን ደግሞ ጸሎት!

**119፡145 "በፍጹም ልቤ"** ይሄንን በሁለት መልክ መረዳት ይቻላል።
1. በሁለንተናዬ (ልክ እንደ ተመሳሳይ ፈሊጥ፣ *መዝ*. 103፡1 ላይ፣ "በእኔ ውስጥ ያለው ሁሉ")
2. "መንታ ሐሳብ" አለመሆኑን ያስረግጣል፣ (*መዝ*. 119፡113) ወይም ግማሽ ልብ ተከታይ (ዳዊትን ልበ ሙሉውን ሰው ከሰሎሞን፣ በእርጅና ዘመኑ ግማሽ ልብ ከሆነው ጋር አነጻጽር)

▣ **"ጌታ ሆይ"** ሦስት የስም ተጠሪዎች አሉ፣ ያህዌን የሚያመለክቱ፣ በዚህ አንጓ ላይ (*መዝ*. 119፡145፤149፤151)። ለ "ያህዌ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

**119፡148** *መዝሙረኛው መተኛት አልቻለም*፣
1. ከእምነተ-ቢስ እስራኤላውያን ጥቃት የተነሣ (ጣዖት አምላኪ ሊሆኑ ይችላሉ)
2. ለእግዚአብሔር ራዕይ (ቃል) ካለው ሙሉ ልባዊ መሰጠት የተነሣ

**119፡149** *መዝሙረኛው ያህዌን እንዲሠራ ይጠይቃል*
1. ከምሕረት ባሕርዩ የተነሣ
2. ከራዕዩ የተነሣ (ማለትም፣ ቅዱስ ቃሉ)
3. ከኃጢአተኞች ስንፍና የተነሣ (ማለትም፣ ይህ ፍትሐዊ ያልሆነና የወደቀ ዓለም)

**119፡152 "ከቀድሞ ጀምሮ"** ይህ የሚያመለክተው
1. የእግዚአብሔርን የጥንት ሥራ (*መዝ*. 24:2፤78:69፤89:11፤102:25፤104:5) እና ለአባቶች የሰጠውን ራዕይ
2. የመዝሙረኛው ረጅም ታሪክ፣ እግዚአብሔርንና ራዕዩን የማወቁና የማመኑ

▣ **"ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም ('ኦላም)።

**መዝሙር ፡119፡153-160 (ሬስ)**

**[153]ሕግህን አልረሳሁምና**
**ችግሬን ተመልከት አድነኝም።**
**[154]ፍርዴን ፍረድ አድነኝም**
**ስለ ቃልህ ሕያው አድርገኝ።**
**[155]መድኃኒት ከኀጥኣን ሩቅ ነው፥**
**ሥርዓትህን አልፈለጉምና።**
**[156]አቤቱ፥ ቸርነትህ እጅግ ብዙ ነው**
**እንደ ፍርድህ ሕያው አድርገኝ።**
**[157]ያሳደዱኝና ያስጨነቁኝ ብዙዎች ናቸው**
**ከምስክር ግን ፈቀቅ አላልሁም።**
**[158]ቃልህን አልጠበቁምና**
**ሰነፎችን አይቼ አዘንሁ።**
**[159]ትእዛዝህን እንደ ወደድሁ ተመልከት**
**አቤቱ፥ በምሕረትህ ሕያው አድርገኝ።**
**[160]የቃልህ መጀመሪያ እውነት ነው፥**
**የጽድቅህንም ፍርድ ሁሉ ለዘላለም ነው።**

**119፡153-160** ተለጣጣቂ የሆኑ (8) ተተኳሪአዊ የጸሎት ጥያቄዎች አሉ፣ በእግዚአብሔር ባሕርይ ላይ በመመሥረት (መዝሙር 119፡156ሀ) እና በመዝሙረኛው ታዛዥነት፣ ለራዕዩ። ይህ የኪዳን ዋነኛ ነገር ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን)።

1-2. ተመልከት፣ መዝ. 119:153፣159 – ቢ.ዲ.ቢ. 906፣ ኬቢ. 1157፣ ቃል ተተኳሪ
3. አድነኝ፣ መዝ. 119:153 – ቢ.ዲ.ቢ. 322፣ ኬቢ. 321፣ ፒል ተተኳሪ
4. ፍርዴን ፍረድ፣ መዝ. 119:154 – ቢ.ዲ.ቢ. 936፣ ኬቢ. 1224፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 35:23-24፤43:1
5. አድነኝ፣ መዝ. 119:154 – ቢ.ዲ.ቢ. 322፣ ኬቢ. 321፣ ፒል ተተኳሪ
6-8. ሕያው አድርገኝ፣ መዝ. 119:154፣156፣159 – ቢ.ዲ.ቢ. 310፣ ኬቢ. 309፣ ፒል ተተኳሪ

**119:153 "ችግሬ"** የችግሩ ርግጠኛ ዓይነት ፈጽሞ አልተቀመጠም፣ ነገር ግን ሁለት ዋነኛ ታሳቢዎች ይኖራሉ።
1. ከእግዚአብሔር የተላከ ችግር፣ እና ጠላቶች (መዝ. 119:67፣71)
2. የግል ጠላቶች (ይህ ይህን ዐውደ-ጽሑፍ በተሻለ ይገጥማል)
   ሀ. ኃጢአተኞች፣ መዝ. 119:155
   ለ. ሥርዓትህን አይፈልጉም፣ መዝ. 119:155
   ሐ. አሳዳጆቼ፣ መዝ. 119:157
   መ. ጠላቶቼ፣ መዝ. 119:157
   ሠ. ተንኮለኞች፣ መዝ. 119:158
   ረ. የእግዚአብሔርን ቃል የማይጠብቁ፣ መዝ. 119:158

**"ሕግህን አልረሳሁምና"** መዝሙራት የተጻፉት ተግባር-ተኮር በሆነው በሙሴ ኪዳን ሥነ-መለኮታዊ ዳርቻ መሆኑን አስታውስ (መዝ. 119:154ለ፣156ለ፣159ለ) መዝሙረኛው እውነተኛነቱን አጉልቶ ያሳያል።
1. ሕግህን አልረሳሁምና፣ መዝ. 119:143፣ መዝ. 119:83፣109፣141
2. ሥርዓትህን አልፈለጉምና፣ እኔ ግን ፈልጌአቸዋለሁ (በአንድምታ)፣ መዝ. 119:155
3. ከምስክሮችህ ወደ ጎን አላልኩም፣ መዝ. 119:157
4. ቃልህን አልጠበቁም፣ እኔ ግን ጠብቄአለሁ (በአንድምታ)፣ መዝ. 119:158
5. ፍርዶችህን እወድዳለሁ፣ መዝ. 119:159

**119:154 "ፍርዴን ፍረድ"** ይህ የፍርድ-ቤት ቃል ነው። አንድ ቀን ንቁ ሕሊና ያለው ሕይወት ሁሉ (መልአካዊ እና ሰው) በእግዚአብሔር ፊት ይቆማል፣ ስለ ሕይወት ስጦታ ምላሽ ይሰጥ ዘንድ (ማቴ. 25:31-46፤2 ቆሮ. 5:10፤ራዕ. 20:11-15)። ሮሜ 8፡31-39 ምናባዊ ምስያውን መዝግቦታል።
1. እግዚአብሔር እንደ ፈራጅ
2. ሰይጣን እንደ ከሳሽ ዐቃቤ ሕግ
3. ኢየሱስ እንደ ጠበቃ፣ ለታማኝ ተከታይ
4. መላእክት እንደ ታዛቢዎች (1 ቆሮ. 4:9፤ኤፌ. 2:7፤3:10)

ይህ አንጓ ደግሞ ያህዌን እንደ "እሚቤዥ ዘመድ" ይገልጸዋል፣ ለዘመዱ ጥብቅና እንደሚቆም (ሌዋ. 25:23-28፤ሩት 3፤ኢዮብ 19:23-27፤ ምሳ. 23:11፤ኤር. 50:34፤51:36፤ሰቆ. 3:58)።

**119:155 "ደኅንነት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት (ብኪ)።

**119:156-157** ሁለቱን ቃላት ተገንዘብ፣ ከተመሳሳይ ሥር የሆኑትን (ቢ.ዲ.ቢ. 912 I)፣ "ታላቅ፣" መዝ. 119:156 እና "ብዙ፣" መዝ. 119:157።

ብዙ ጠላቶች አሉ (መዝ. 119:157) ግን ደግሞ ታላቅ አምላክ አለ (መዝ. 119:156)። ይኸው ተመሳሳይ እውነት 1 ጴጥሮስ ላይ በአንድ ቃል ተገልጿል፣ እዚያም (ኅብረ-ቀለም) የሚለው የሚገልጸው

1. የበዛ ፈተና፣ 1 ጴጥ. 1:6
2. የበዛ የእግዚአብሔር ጸጋ፣ 1 ጴጥ. 4:10

**119፡159 "እኔ. . .ጠላኋቸው"** ይህ ለአኪ. አማኞች የማያስደስት ነው። ነገር ግን ሙሴአዊ ኪዳን መሆኑን አስታውስ። የሰው ስሜቶች ዘወትር በግነታዊ ዘይቤ ይቀመጣሉ። መዝሙረኛው ለእግዚአብሔርና ለቃሉ ያለው ፍቅር ጽኑ ምላሽ እንዲሰጥ አድርጎታል (መዝ. 139፡21)

1. በማይቀበሉት ላይ
2. የተመረጠውን ክፍል ብቻ የሚቀበሉትን
3. በግብዝነት የሚሄዱትን

እግዚአብሔር ራሱ የገዛ ራሱን አቋም ገልጿል (መዝ. 95፡10) የእርሱን ራዕይ (ቃል) በማይቀበሉት ላይ፣ ሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30 ላይ። ብዙ ከተሰጠው ብዙ ይጠበቃል (ሉቃስ 12፡48)። የመዝሙረኛው ጠላቶች የእስራኤል ሰዎች ሳይሆኑ አይቀሩም።

**119፡160** እዚህ ቁጥር ላይ ግሥ የለም። አአመመቅ ሁለት "የመሆን" ግሦችን ይሰጣል።

▣ ***"ሁሉም"*** ይህ ማለት "በሙሉ" ነው፣ እሱም ከቀጣዩ የቅኔ ስንኝ ጋር የተሻለ ትይዩ የሚፈጥር ከ "ጭብጥ" ይልቅ።

▣ **"እውነት"** ይህ እውነት አልያም/በተቃርኖ ውሸት አይደለም፣ ነገር ግን ታማኝነት አልያም/በተቃርኖ ያልታመነ መሆን እንጂ። የእግዚአብሔር ቃል ቀጥተኛ ተቃራኒ ነው፣ ለወደቀው ሰው ቃል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን እና ታማኝነት በብኪ።

▣ **"ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (አላም)።

▣ **"ጻድቅ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጻድቅ።

***መዝሙር ፡119፡161-168 (ሳን)***

**[161]ገዦዎች በከንቱ አሳደዱኝ**
**ከቃልህ የተነሣ ግን ልቤ ደነገጠብኝ።**
**[162]ብዙ ምርኮ እንዳገኘ**
**በቃልህ ደስ አለኝ።**
**[163]ዓመፃን ጠላሁ ተጸየፍሁም**
**ሕግን ግን ወደድሁ።**
**[164]ስለ ጽድቅህ ፍርድ**
**ሰባት ጊዜ በቀን አመሰግንሃለሁ።**
**[165]ሕግህን ለሚወድዱ ብዙ ሰላም ነው፥**
**ዕንቅፋትም የለባቸውም።**
**[166]አቤቱ፥ ማዳንህን ተስፋ አደርግሁ፥**
**ትእዛዛትህንም ጠበቅሁ።**
**[167]ነፍሴ ምስክርህን ጠበቀች**
**እጅግም ወደደችው።**
**[168]መንገዶቼ ሁሉ በፊትህ ናቸውና**
**ትእዛዝህንና ምስክርህን ጠበቅሁ።**

**119፡161-168** ይህ አንዳ ባሕርይ ያደረገው የተጠናቀቁ ግሦችን ነው፣ ይኸውም የተጠናቀቀ፣ የተፈጸመ፣ የተከናወነ ድርጊትን የሚገልጽ። መዝሙረኛው ምን እንደሆነ ያስረግጣል፣ በእግዚአብሔርና በራዕዩ (ቃሉ) የተነሣ።

1. ከቃልህ የተነሣ ልቤ ደነገጠብኝ፣ መዝ. 119:161ለ፣ መዝ. 119:120
2. በቃልህ ደስ አለኝ፣ መዝ. 119:162ሀ
3. ዓመፃን ጠላሁ ተጸየፍሁም፣ መዝ. 119:163ሀ፣ መዝ. 119:104፤118፤ምሳ. 13:5
4. ሕግህን ወደድሁ፣ መዝ. 119:163ለ
5. አመሰግንሃለሁ፣ በቀን ሰባት ጊዜ መዝ. 119:164ሀ
6. የሚወድዱ (ማለትም፣ መዝሙረኛውም አንደኛቸው ነው) ሕግህን፣ መዝ. 119:165ሀ
7. ማዳንህን ተስፋ አደርጋለሁ፣ መዝ. 119:166ሀ
8. ትእዛዛትህን አደረግሁ፣ መዝ. 119:166ለ
9. ነፍሴ ምስክሮችን ጠበቀች፣ መዝ. 119:167ሀ
10. ምስክሮችህን ወደድኩ፣ መዝ. 119:167ለ
11. ፍርዶችህንና ምስክሮችህን ጠበቅሁኩ፣ መዝ. 119:168ሀ
12. መንገዴ ሁሉ በፊትህ ነው፣ መዝ. 119:168ለ

**119፡161ሀ** "አለቆች" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 978) ሰፊ የፍቺ አጠቃቀም አለው፣ እሱም የሲቪል፣ የነገድ፣ እና ሃይማኖታዊ መሪዎችን የሚያጠቃልል (መዝ. 119፡23)። የመዝሙር 119 ጸሐፊ ከዚህ ማኅበራዊ ምድብ አይደለም፣ እናም ዘወትር በሥልጣን ላይ ባሉ ሰዎች ይሳደዳል።

**119፡161ለ** አስገራሚ የሚሆነው፣ ይህ የቅኔ ስንኝ የሚገልጸው የእግዚአብሔርን ራዕይ ስለ መፍራት መሆኑ ነው፣ እንዲሁም የሚቀጥለው ስንኝ በእርሱ ስለ መደሰት ይናገራል። ርግጥ እነዚህ ሁለቱም ስሜቶች ስለ ቅዱስ ቃሉ እውነት ናቸው። እሱም በወደቀው የሰው ልጅ ላይ ፍርሃትን፣ ተስፋን፣ ሰላምን፣ እና ደስታን ያመጣል!

ጄፒኤስኦኤ "በፍርሃት ቆሞ" በሚል ይተረጉመዋል (ቢዲቢ 808፣ ኬቢ 922፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) እንደ "ልቤ በቃልህ ፍርሃት ተደሰተች" ከመዝ. 119:162*ሀ ጋር* ትይዩ ለመፍጠር።

**119:162ለ** ብልጽግናው ከሥጋዊ ነገሮች *ጋር* አይያያዝም ነገር ግን የእግዚአብሔርን *ራዕይ* ከማወቅና በእርሱ ላይ *ለመሥራት* ካለ ፍቃደኝነት እንጂ!

**119፡163 "ሰባት ጊዜ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተምሳሊታዊ ቁጥሮች በቅዱስ ቃሉ።

**119፡165** ይህ ቁጥር ሁለት የተለዩ ጠቀሜታዎችን ይሰጣል፣ የእግዚአብሔርን *ራዕይ* በመውደድ።

1. *ታላቅ* ሰላም (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰላም [ሻሎም])
2. ለማሰናከያ አይሰጥም (ቢዲቢ 506)

ይሄንኑ ተመሳሳይ እውነት ለመግለጽ ሌለኛው መንገድ ምሳ. 3፡1-12፤13-26 ላይ ይገኛል፣ ይኸውም የአባትን ትምህርትና ጥበብን በመጠቀም! እግዚአብሔርን ማወቅና መከተል በዚህ ሕይወትም ሆነ በሚመጣው ጠቀሜታን ያመጣል!

"ማሰናከያ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 506) ከእግዚአብሔር ራዕይ ጽንሰ-ሐሳብ ፈሊጥ *ጋር* እንደሚዛመድ አስታውስ፣ በግልጽ እንደ ተመለከተ፣ የለዘበ፣ ቀና፣ እና ማሰናከያ እንደሌለበት መንገድ (መዝ. 119:105፤ምሳ. 6:23)።

**119:166** የዚህ ቁጥር ትይዩ "መናፈቅ" የሚለው መዝ. 119:174 *ጋር* ነው። የእግዚአብሔር ማዳን የወደፊት ነው፣ ግን ርግጠኛ! ቃል የገባውን ያደርጋል (በግለሰብም ሆነ በወል)።

**119፡167 "መጠበቅ"** *መታዘዝ* ዋነኛ ነገር ነው፣ በሁለቱም በብኪ እና አኪ። አዲስ ኪዳን (አኪ ወንጌል) የኤር. 31፡31-34 ዘዴውን ቀይሮታል፣ ዓላማውን ሳይሆን። እግዚአብሔር ሕዝብን ይፈልጋል፣ የእርሱን ባሕርይ ለአሕዛብ እንዲያንጸባርቅ፣ ወደ እርሱ እንዲመጡና እንዲድኑ! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ።

*ግሡ* (ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) መዝ. 119:168 ላይ ተደግሟል፣ ለአጽንዖት!

**119፡168ለ** ተመሳሳይ እውነት የመዝሙር 139 ይዘት ነው። እግዚአብሔር በሙሉ ያውቀዋል፣ የልዩ ፍጡሩን የእያንዳንዱን ልብ እና ሐሳብ (ማለትም፣ ሰዎች፣ 1 ሳሙ. 16:7፤1 ነገ. 8:39፤1 ዜና. 28:9፤መዝ. 7:9፤17:3፤66:10፤ኤር. 11:20፤17:10፤20:12፤ሉቃስ 16:15፤ሐዋ. 1:24)።

## *መዝሙር* ፡119፡169-176 (*ታው*)

**[169]አቤቱ፥ ጸሎቴ ወደ ፊትህ ትቅረብ**
**እንደ ቃልህም አስተዋይ አድርገኝ።**
**[170]ልመናዬ ወደ ፊትህ ትድረስ**
**እንደ ቃልህ አድነኝ።**
**[171]ሥርዓትህን አስተምረኸኛልና**
**ከንፈሮቼ ምስጋናን አወጡ።**
**[172]ትእዛዛትህ ሁሉ ጽድቅ ናቸውና**
**አንደበቴ ቃልህን ተናገረ።**
**[173]ትእዛዛትህን መርጫለሁና**
**እጅህ የሚያድነኝ ይሁን።**
**[174]አቤቱ፥ ማዳንህን ናፈቅሁ**
**ሕግህም ተድላዬ ነው።**
**[175]ነፍሴ ትኑርልኝ ታመሰግንህማለች፥**
**ፍርድህም ይርዳኝ።**
**[176]እንደ ጠፉ በግ ተቅበዘበዝሁ**
**ትእዛዛትህን አልረሳሁምና ባሪያህን ፈልገው።**

**119፡169-176** ይህ የመጨረሻ አንጓ የተጽኝኗዊ ባሕርይ ያለበት ነው፣ ሦስቱ ተተኳሪዎች ይከተሏቸዋል
(መዝ. 119:169፣170፣176)።

1. ጩኸቴ ወደ ፊትህ ትቅረብ፣ መዝ. 119:169*ሀ* – ቢዲቢ 897፣ ኬቢ 1132፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. አስተዋይም አድርገኝ፣ መዝ. 119:169ለ – ቢዲቢ 106፣ ኬቢ 122፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
3. ልመናዬ ወደ ፊህ ትድረስ፣ መዝ. 119:170*ሀ* – ቢዲቢ 97፣ ኬቢ 112፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፤ ትይዩውን ተመልከት በመዝ. 119:169 እና 170*ሀ* መካከል ያለውን
4. አድነኝ፣ መዝ. 119:170ለ – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
5. ከንፈሮቼ ምስጋናን አወጡ፣ መዝ. 119:171*ሀ* – ቢዲቢ 615፣ ኬቢ 665፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
6. አንደበቴ ይዘምር፣ መዝ. 119:172*ሀ* – ቢዲቢ 777፣ ኬቢ 854፣ *ቃል ተጽዕኗዊ*
7. እጅህ የሚያድነኝ ይሁን፣ መዝ. 119:173*ሀ* – ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ *ቃል ተጽዕኗዊ*
8. ነፍሴ ትኑርልኝ፣ መዝ. 119:175*ሀ* – ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ *ቃል ተጽዕኗዊ*

9. አንተን አመሰግን ዘንድ፣ መዝ. 119:175ሀ – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ፒል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
10. ፍርድህም ይርዳኝ፣ መዝ. 119:175ለ – ቢዲቢ 740፣ ኬቢ 810፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
11. ባርያህን ፈልገው፣መዝ. 119:176ሀ – ቢዲቢ 134፣ ኬቢ 152፣ ፒል ተተኳሪ

መዝሙሩ የሚደመድመው በበዛ የጸሎት ጥያቄ ነው!

**119፡171-173** የእያንዳንዱ ቁጥር ሁለተኛ ስንኝ የጥያቄውን ምክንያት እንዴት እንደሚያብራራ ተገንዘብ።

**119፡176ሀ** ይህ የእግዚአብሔርን ሕዝብ እንደሚቅበዘበዝ በግ የሚያሳየው ምናባዊ ምስያ ደግሞ ኢሳ. 53:6፤ኤር. 50:6፤ሕዝ. 34:2-19፤ዘካ. 10:2-3 ላይ ይገኛል። ይህም ምናባዊ ምስያነቱ

1. እግዚአብሔር እንደ እረኛ – መዝሙር 23፤ሕዝቅኤል 34
2. መሲሑ እንደ እረኛ – ዘካርያስ 10-11፤ዮሐንስ 10:1-18

ተቀምጧል። በጎች ቋሚ፣ ግላዊ፣ የጥበቃ ክብካቤ ይሻሉ!

የመዝ. 119:176ለ ተተኳሪ ማቴ. 18:12-14 እና ሉቃስ 15:4-7 ያስታውሳል። እግዚአብሔር የጠፉትን በጎች ይፈልጋል! ሃሌሉያ!

# መዝሙር 120
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ከተንኮለኛ ለመታደግ ጸሎት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የመዓርግ ጸሎት | ልመና ከመራር ጠላቶች ለማረፍ | የስደተኛ ጸሎት ከጠላቶች ለመታደግ (ሰቆቃ) | የዕርዳታ ጸሎት | የሰላም ጠላቶች |
| 120:1-4 | 120:1-2 | | | |
| | 120:3-4 | 120:1-2 | 120:1-2 | 120:1-2 |
| 120:5-7 | 120:5-7 | 120:3-4 | 120:3-4 | 120:3-4 |
| | | 120:5-7 | 120:5-7 | 120:5 |
| | | | | 120:6-7 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 120፡1-4**

**1በተጨነቅሁ ጊዜ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ፥**
**ሰማኝም።**
**2ከዓመፀኛ ከንፈር**
**ከሸንጋይም አንደበት፥ አቤቱ፥ ነፍሴን አድናት።**
**3ስለ ሸንገላ አንደበት**
**ምንም ይሰጡሃል? ምንስ ይጨምሩልሃል?**
**4እንደ በረሃ እንጨት ፍም**
**የኃያላን ፍላጾች የተሳሉ ናቸው።**

**120፡1 "በተጨነቅሁ ጊዜ"** በርግጠኝነት ምን ዓይነት መከራ እንደሆነ (ቢዲቢ 865 I፣ አንስታይ ስም) አልተቀመጠም፣ ነገር ግን ሊዛመድ የሚችለው

1. ዓመጸና ከንፈር መዝ. 120፡2ሀ
2. ሸንጋይ አንደበት፣ መዝ. 120፡2ለ፣3ለ

የተዛማጁ ግሥ ሥርወ-ቃላዊው መነሻ (ቢዲቢ 864) የሚገልጸው የሚያስር ወይም የሚያግትን ነው። በዘይቤአዊነት ጥቅም ላይ ሲውልም ጠባብ፣ ጥብቅ ለሆነ ነገር፣ ወይም ለሚያጨናንቅ ስፍራ ነው። ተመሳሳይ ሥር ለባላንጣ ወይም ለጠላት ጥቅም ላይ ይውላል (ቢዲቢ 865 III)።

ይህ የ "ክልከላ" ጽንሰ-ሐሳብ የዕብራይስጡ ምናብ ተቃራኒ ነው፣ የሰፊነት፣ ግልጽነት፣ እና ነጻነት።

▣ **"ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ"** በመከራ ጊዜ ታማኝ ተከታዮች ወደ ያህዌ በጸሎት ይመለሳሉ፣ እሱም ይሰማቸዋል (ግሦቹ ያለፈ ሁነትን ይገልጻሉ)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ውጤታማ ጸሎት።

የመለኮት ስሙ ያህዌ ነው፣ ለእስራኤል አምላክ የኪዳን ስም። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

**120:2 "ነፍሴን አድናት"** ግሡ (ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717) ሂፊል ተተኳሪ ነው። እሱም የተጠናከረ ጸሎትን ያመለክታል። የዚህ ሥር መሠረታዊ ፍች ሂፊል ላይ "መንጠቅ" ነው። ምርኮን ከማራኪው አፍ እንደማለት።

"ነፍስ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 659) ኔፊሽ ነው፣ እሱም የሕይወትን ኃይል የሚገልጽ። ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት ድረ-ገጽ ላይ ዘፍ. 35:18።

▣ **"ዓመጸኛ ከንፈር… ሽንጋይ አንደበት"** እነዚህ በዕብራይስጥ ተመሳሳይነት ትይዩ ዝምድና አላቸው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የዕብራይስጥ ቅኔ።

**120:3** መዝሙረኛው በቀጥታ ባላንጣዎቹን ይነግራቸዋል። እሱም ያህዌ የሚገባቸውን እንደሚሰጣቸው ያስረግጣል (ኤቢ፣ ገጽ 196፤ ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ 1048)።

**120:4** የመዝ. 120:4 ምናባዊ ምስያ ለመዝ. 120:3 ጥያቄ ምላሽ መስጠት ነው። ያህዌ በዚህ መልኩ ነው "ለውሸተኛ ከንፈሮች" ምላሽ የሚሰጠው (መዝ. 7:13)።

**መዝሙር ፡ 120:5-7**

> **5 መኖሪያዬ የራቀ እኔ ወዮልኝ**
> **በቄዳር ድንኳኖች አደርሁ።**
> **6 ሰላምን ከሚጠሉ ጋር**
> **ነፍሴ ብዙ ጊዜ ኖረች።**
> **7 እኔ ሰላማዊ ነኝ በተናገርኋቸው ጊዜ ግን**
> **በከንቱ ተሰለፉብኝ።**

**120:5 "ሜሴክ… ቄዳር"** እነዚህ የብዝበዛ ምሳሌዎች ይመስላሉ (ሕዝ. 27:13፣21)። መዝሙረኛው ለባላንጣዎቹ ጠበኛ፣ በኃጢአት የተሞላ መለያን ይሰጣቸዋል፣ ለእነዚህ ብሔራዊ ወገኖች።

ሌላው አማራጭ እነዚህን በመልከዓ-ምድራዊ ትይዩዎች አድርጎ መመልከት ነው፣ አንደኛው ወደ ሰሜን ጫፍ፣ ሌላው ወደ ደቡብ። እንደዚያ ከሆነ፣ እሱ ምስያ የሚሆነው

1. "ከእነዚህ በጥላቻ ከተሞሉ ሰዎች አርቀህ አድነኝ"
2. "አቤቱ ከመቅደስ እንድርቅ አታርገኝ"

**120:6-7** ይህ የመዝሙረኛውን አጥቂዎች ፍንጭ ይሰጣል፣ የፖለቲካ ጠላት እንደሆኑ፣ ወታደራዊ ግጭትን የሚሹ።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ማነው መዝሙረኛውን የሚያጠቃው?
2. የመዝ. 120:4ን ምናባዊ ምስያ አብራራ።
3. ሁለት የጎሳ ወገሞች ለምን ተጠቀሱ፣ መዝ. 120:5 ላይ?
4. መዝ. 120:6 እና 7 ታሳቢውን ታሪካዊ መቼት እንዴት ያብራራሉ ወይም ይገልጻሉ?

# መዝሙር 121
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር የእስራኤል ጠባቂ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የመዓርግ መዝሙር | እግዚአብሔር ለሚፈልጉት ረዳት ነው | የባርኮት ደንብ | እግዚአብሔር ጠባቂያችን | የእስራኤል ጠባቂ |
| 121:1-4 | | | | |
| | 121:1-2 | 121:1-2 | 121:1-2 | 121:1-2 |
| | 121:3-4 | 121:3-4 | 121:3 | 121:3-4 |
| | | | 121:4-6 | |
| 121:5-8 | | | | |
| | 121:5-6 | 121:5-6 | | 121:5-6 |
| | 121:7-8 | 121:7-8 | 121:7-8 | 121:7-8 |

### **የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛ አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 121፡1-4**

**1ዓይኖቼ ወደ ተራሮች አነሣሁ**
**ረዳቴ ከወዴት ይምጣ?**
**2ረዳቴ ሰማይና ምድርን ከሠራ**
**ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው።**
**3እግርህን ለመናወጥ አይሰጠውም**
**የሚጠብቅህም አይተኛም።**
**4እነሆ፥ እስራኤልን የሚጠብቅ**
**አይተኛም አያንቀላፋምም።**

**121፡1-8** ግሦቹ ሁሉ ያልተጠናቀቁ ናቸው። እነርሱም በሂደት ላይ እና ቀጣይነት ያለውን መለኮታዊ ክብካቤና ጥበቃ የሚገልጹ።

ግምት አለ፣ በዚህ መዝሙር ላይ ምን ያህል ተናጋሪዎች መኖራቸው ላይ በመመሥረት፣ ያም መዝ. 121፡3 ላይ ያልተጠናቀቁት ጥቅም ላይ የዋሉት በተጽዕኗዊ መልኩ ነው (ማለትም፣ የጸሎት ጥያቄዎች፣ አኢመቅ፣ አእት)።

**121፡1 "ዓይኖቼን አነሣሁ"** ይህ ምናባዊ ምስያ የሚገልጸው ሰው እንዴት እንደሚታመን ነው (መዝ. 123፡1፤ 141፡8)።

▣ **"ወደ ተራሮች"** የብዙ ቁጥር እንደሆነ ተገንዘብ፣ የሚገልጸውም
1. ፍጥረትን፣ መዝ. 87፡1
2. ሞሪያ ተራራ ላይ ያለ ቤተ-መቅደስ (ማለትም፣ የግርማዊነቱ ብዙነት፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሞሪያ)

3. የጥንካሬ፣ ጽናት፣ እና የረዥም ዕድሜ ምናባዊ ምስያ
4. ጥበቃ (መዝ. 125፡1-2)
5. የኤምቲ መግቢያ፣ "የከፍታ መውጣት መዝሙር" ማለትም ወደ ኢየሩሳሌም ሲኬድ የምነና መዝሙር ከሆነ፣ እንግዲያውስ የይሁዳን ኮረብቶች መመልከት ማለት ወደ መቅደስ ተቃርበዋል ማለት ነው
6. እሱም በከፍታ ስፍራዎች ላይ የሚደረገውን የበአል አምልኮ መቃረን ማለት ሊሆን ይችላል (2 ነገ. 23፡4-14)። አንዳንዶች ወደ መራባት ጣዖት ይመለከታሉ፣ ነገር ግን ታማኝ ተከታዮች ያህዌን ብቻ ነው የሚመለከቱት። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አህዳዊነት።

▣ **"ረዳቴ ከወዴት ይምጣ"** መዝሙር 221፡2 ግልጽ አድርጎታል፣ ርዳታው ሥጋዊ ተራራ ሳይሆን የፍጥረት አምላክ ለመሆኑ (መዝ. 121፡2) እና ኪዳን (መዝ. 121፡4)።

**121፡2 "እግዚአብሔር"** ይህ የኪዳን ስም ነው ለመለኮት — ያህዌ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ **"ሰማይና ምድርን ከሠራ"** ይህ የዚህን ዓለም አካላዊ አፈጣጠር ያመለክታል (መዝ. 102:25፤115:15፤ 124:8፤134:3፤146:6)። ይህም የዘፍጥረት 1 ጠቃሽ ነው።

ያህዌ ባሕርዩ እንዴት እንደሆነ ተገንዘብ

1. ፈጣሪ፣ መዝ. 121:2
2. መጋቢ፣ መዝ. 121:3ሀ፣51
   ሀ. ግለሰብን፣ መዝ. 121:7ለ፣8
   ለ. በአጠቃላይ፣ መዝ. 121:4
3. ንቁ ጠባቂ፣ መዝ. 121:3ለ
4. መጠለያ፣ መዝ. 121:5-6 (ልዩ ርዕስ ተመልከት: ጥላ እንደ መጠበቂያና ክብካቤ ዘይቤ)
5. ዘላለማዊ ጠባቂ፣ (ግሥ፣ ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ መዝ. 121:3፣4፣5፣7 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል [ሁለቴ]፣ እና 8)።

**121፡3 "እግር ለመናወጥ"** ይህ የተለመደ የዕብራይስጥ ምስያ ነው፣ እሱም

1. ስለ መልካም ሕይወት የሚናገር እንደ ግልጽ፣ ቀና፣ የተስተካከለ መንገድ/ፍኖት/ፈለግ የሆነ(መዝ. 139፡24)
2. ስለ ክፉ የሚናገር፣ እሱም ግልጽ ሆኖ ከተመለከተው የእግዚአብሔር መንገድ የሚያፈነግጥ (ማለትም፣ መገለጥ) ወይም በመንገድ ላይ የሚሰናከል

▣ **"አያንቀላፋም"** እግዚአብሔር ዘወትር ይጠብቃል

1. ፍጥረቱን
2. ሕዝቡን

እንደ በአል የሚተኛ ሳይሆን፣ 1 ነገ. 18:27፤ሕዝ. 6:13፤18:6፣12፣15። "መተኛት" ዘይቤ ሊሆን ይችላል፣ ያህዌ በማይሠራበት ጊዜ (መዝ. 7:6፤ 44:23፤73:20፤78:65)። ሆኖም፣ በራሱ ጊዜ ለሕዝቡ ይሠራል።

መዝሙር 121:4 ይሄንን ተመሳሳይ እውነት ይደግመዋል፣ በተጠቃለለ መልኩ። እግዚአብሔር ለእስራኤል ዕቅድ አለው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

**መዝሙር ፡ 121፡5-8**

**5 እግዚአብሔር ይጠብቅሃል፥**
**እግዚአብሔርም በቀኝ እጅህ በኩል ይጋርድሃል።**
**6 ፀሐይ በቀን አያቃጥልህም**
**ጨረቃም በሌሊት።**
**7 እግዚአብሔር ከክፉ ሁሉ ይጠብቅሃል፥**
**ነፍስህንም ይጠብቃታል።**
**8 ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም**
**እግዚአብሔር መውጣትህና መግባትህን ይጠብቃል።**

**121፡6** ይህ ምናባዊ ምስያነቱ

1. ለወታደራዊ ጥቃት
2. ለአጋንንታዊ ጥቃት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አጋንንታዊ በብኪ)

"መከላከል/መጠበቅ ከክፉ ሁሉ" የሚለውን ሐረግ ተገንዘብ፣ መዝ. 121፡7ሀ ላይ። በርግጠኝነት ሊሆን የሚችለው ይህ ሐረግ የዕብራይስጥ ፈሊጥ መሆኑን ነው፣ ለችግሮች ሁሉ።

**121፡7 "ነፍስህንም ይጠብቃታል"** እንዴት ያለው አስደናቂ ተስፋ ነው፣ ለግለሰብ ክብካቤና ጥበቃ! እሱ "ከ" እና "ለ" ታማኝ ተከታዮች ነው። ብቻችንን አይደለንም እናም ሕይወታችን ዓላማ አለው!

**121፡8ሀ** ይህ የዕብራይስጥ ምናባዊ ምስያ ነው፣ ለእግዚአብሔር ንቁ ጥበቃና ክብካቤ፣ በሕይወት ዘመናቸው ሁሉ፣ ለታማኝ ተከታዮቹ (ዘዳ. 28:6፤139:1-6)

ሁነኛውን የዕብራይስጥ የሁለት ተቃራኒዎችን አጠቃቀም መንገድ ተገንዘብ፣ እንደ ሁሉንም ማካተቻ መንገድ።

1. ሰማይ — ምድር፣ መዝ. 121፡2

2. ፀሐይ — ጨረቃ፣ መዝ. 121፡6
3. ውስጥ — ውጭ፣ መዝ. 121፡8

**121፡8ለ** በርግጠኝነት በዚህ ቁጥር ላይ የዘላለማዊነት ይዘት አለ፣ መዝ. 23፡6 ላይ እንዳለው። ከሞት በኋላ ያለው ሕይወት በብኪ. ተገልጧል፣ ነገር ግን ቀጣይነት ያለው የአኪ መገለጥ እውነቱን ግልጽ አድርጎታል!

▣ **"ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም ('ኦላም)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የትኛውን ተራራ ወይም ተራራዎች ነው መዝ. 121፡1 የሚጠቅሰው?
2. እግዚአብሔር እንደ ፈጣሪ እዚህ መዝሙር ላይ ለምን ተጠቀሰ?
3. የመዝ. 121፡3ሀ የብኪ. ምናባዊ ምስያ አብራራ።
4. እስራኤል ወደዚህ መዝሙር ለምን ሊመጣ ቻለ፣ መዝ. 121፡4 ላይ? የጥበቃና የክብካቤ አጠቃላይ ገጽታ እንዴት ይተገበራል?
5. "ጥላ" የሚለውን ምናባዊ ምስያ አብራራ፣ መዝ. 121፡5ለ ላይ።
6. "ክፉ ሁሉ" የሚለው መዝ. 121፡7ሀ ላይ ያለው ምንድነው የሚጠቅሰው?
7. ከሞት በኋላ ላለ ሕይወት የሚጠቅስ አለውን መዝ. 121፡8ለ ላይ?

# መዝሙር 122
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጸሎት ለኢየሩሳሌም ሰላም <u>ኤምቲ መግቢያ</u> የዳዊት የመዓርግ መዝሙር 122:1-5 | ወደ እግዚአብሔር ቤት በመሄድ ያለ ደስታ | ጽዮንን የማመስገን ዝማሬ እንደ መናኞች ግብ | ኢየሩሳሌምን በማመስገን | ሰላም ለኢየሩሳሌም |
| 122:6-9 | 122:1-2 | 122:1-2 | 122:1-2 | 122:1-2 |
| | 122:3-5 | 122:3-5 | 122:3-5 | 122:3-5 |
| | 122:6-9 | 122:6-9 | 122:6-9 | 133:6-7 |
| | | | | 122:8-9 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 122፡1-5**

**1ወደ እግዚአብሔር ቤት እንሄድ**
**ባሉኝ ጊዜ ደስ አለኝ።**
**2ኢየሩሳሌም ሆይ፥**
**እግሮቻችን በአደባባይሽ ቆሙ።**
**3ኢየሩሳሌምስ እርስ በርስዋ**
**እንደ ተገጠገጠች ከተማ ተሠርታለች።**
**4የእግዚአብሔርን ስም ያመሰግኑ ዘንድ፥**
**ለእስራኤል ምስክር ሊሆኑ**
**የእግዚአብሔር ነገዶች ወደዚያ ይወጣሉ።**
**5ዙፋኖች በዚያ ለፍርድ ተቀምጠዋልና፥**
**የዳዊት ቤት ዙፋኖች።**

**122፡1 "ባሉኝ ጊዜ"** ይህ መዝሙር የሚገልጸው ወደ መቅደስ የሚደረገውን ጉዞ (ምነና) ነው፣ ምናልባትም በዓመታዊ በዓል ቀን (መዝ. 122፡4፤ ሌዋውያን 23) ወይም በተለየ የተጠራ ሁኑት።

"እነርሱ" የሚያመለክተው

1. ተጓዥ ሰዎች (መናኞች) በጉዞ ላይ እንዳሉ፣ ወደ ኢየሩሳሌም
2. የአካባቢው ሌዋውያን ወደ ኢየሩሳሌም የሚመጡትን መናኞች እንኳን ደኅና መጣችሁ ሲሉ
3. የባርኮት ደንብ ምስያ

ኢየሩሳሌም "ልዩ ስፍራ" ነበረች፣ ለእግዚአብሔር ማደሪያነት፣ በተባበረው መንግሥት እና በተከፋፈለው መንግሥት። ከባቢሎን ስደት በኋላ እና አይሁድ እንዲመለሱ ከተፈቀደ ወዲህ (ማለትም፣ የሲረስ አዋጅ፣ 538 ቅ.ል.ክ)። እሷ እጅግ የከበረች ሆነች፣ ለተመለሱት እስራኤላውያን።

**122፡2** "የእግሮች" ወይም "መራመድ" ምስያነት የመልካም ሕይወት ሥነ-መለኮታዊ ቋንቋ ክፋይ ነው። የእግዚአብሔር ፍቃድ አጥርቶ የተገለጠ መንገድ ነው። የመዳረሻ ግቡም በእግዚአብሔር ፊት በመቅደሲጋ መድረስ ነው። ይህም ደግሞ ከእግዚአብሔር ጋር ላለ እስከ ሕይወት ፍጻሜ ለሚደርስ ኅብረት ይሠራል (ኢዮብ 14:13-17፤መዝ. 23:4-6)።

▣ **"ኢየሩሳሌም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሞሪያ፣ ሳሌም፣ ጀቡስ፣ ጀሩሳሌም፣ ጽዮን።

**122፡3** ይህ ያልተለመደ ቁጥር ነው። በርግጠኝነት ምን እንደሚረጋገጥ ወይም እንደሚመሰገን ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። ግሡ (ቢዲቢ 287፣ ኬቢ 287፣ ፖል የተጠናቀቀ) በመሠረቱ ጥቅም ላይ የሚውለው ነገሮችን ለማገናኘት ነው። ፑኣል ላይ እሱ የሚገልጸው

1. የማደሪያው ድንኳን መጋረጃ — ዘጸ. 28፡7
2. ከድኅረ-ስደት በፍጥነት የተገነባ የኢየሩሳሌም ቅጥር — ነህ. 4፡6
3. ባለ ቃል ኪዳን ወዳጆች — መዝ. 94፡20
4. አንድ ላይ የሚኖሩ ሰዎች — መክ. 9፡4

እዚህጋ የሚገልጸው ደኅና ቅያስ እና በደንብ የተገጠገጠ የከተማ ፕላንን ነው።

**122፡4** ዘዳግም ላይ ሙሴ እስራኤላውያንን የሳስባቸዋል፣ ያህዌን ለማምለክ የተወሰነ ስፍራ እንዲሄዱ (ምሳ. ዘዳ. 16፡16)። ቁጥሩ እነዚህን ዓመታዊ የአምልኮ ስብሰባዎች ይጠቅሳል (ሌዋውያን 23)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"ሕግ"** |
| **አኪጀቅ፣ LXX፣** | |
| **ፔሺታ** | **"ምስክር"** |
| **አየተመቅ** | **"ተደነባ"** |
| **አእቅ** | **"ትእዛዝ"** |
| **አኢመቅ** | **"ምልክት"** |
| **ጀፒኤስአኤ** | **"ታዘዘ"** |
| **የተእመቅ** | **"ተግባር"** |

ይህ አንስታይ ስም (ቢዲቢ 730) ዘወትር የሚተረጎመው "ምስክር" በሚል ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ለእግዚአብሔር ራዕይ ጥቅም ላይ የዋሉ ቃላት።

አስገራሚ የሚሆነው ሙባጥ (ሙት ባሕር ጥቅሎች) የእጅ ጽሑፍ "የእስራኤል ማኅበረሰብ" የሚል መያዙ ነው፣ በስም ሐረጉ ምትክ። አንዳንድ ተርጓሚዎች የሚገምቱት መዝ. 122፡3ለ ደግሞ የሚጠቅሰው "የተባበሩትን ሕዝቦች" ማኅበረሰብ ነው።

▣ **"እስራኤል"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እስራኤል (ስሙ)።

▣ **"ያመሰግኑ ዘንድ"** ይህ የሚያመለክተው

1. የአምልኮ ሥርዓት
2. መሥዋዕት ማቅረብ (መሥዋዕት)

▣ **"የእግዚአብሔርን ስም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ።

መዝሙር 122፡4ሐ ላይ ሙሉው የኪዳን ስም — ያህዌ (ቢዲቢ 217) ጥቅም ላይ ውሏል፣ ነገር ግን ምሕጻረ-ቃሉ — ያህ (ቢዲቢ 219) ጥቅም ላይ የዋለው 122፡4ሀ ላይ ነው።

**122፡5 "ዙፋን"** የሚወክለው

1. ሕጋዊ ውሳኔዎች — ዘዳ. 17፡8
2. ንግሥና – መዝ. 89:4፣29፣36፤132:12

እግዚአብሔር ለዳዊት ስለ ዘሮቹ የሰጠው ተስፋ 2 ሳሙኤል 7 ላይ ይገኛል፤ እንዲሁም መሲሐዊ ገጽታው ኢሳይያስ 9፤ 11፤ ሚክያስ 5 ላይ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሲሕ።

**መዝሙር ፡ 122፡6-9**

**6 ለኢየሩሳሌም ሰላምን ለምኑ**
**አንተንም ለሚወድዱ ልማት ይሁን።**
**7 በኃይልህ ሰላም፥**
**በጌጠኛ ቤትህም ልማት ይሁን።**
**8 ስለ ወንድሞቼ ስለ ባልንጀሮቼም፥**
**በውስጥሽ ሰላም ይሁን አልሁ።**
**9 ስለ አምላካችን ስለ እግዚአብሔር ቤት**
**ላንቺ መልካምነትሽን ፈለግሁ።**

**122፡6-9** ይህ አንጓ የጸሎት ጥሪን ይገልጻል።

1. ቃል ተተኳሪ – መዝ. 122:6ሀ
2. ሁለት ተጽዕኗዊዎች – መዝ. 122:6b፣7ሀ
3. ሁለት ተጓዳኞች – መዝ. 122:8ለ፣9ለ

ኢየሩሳሌም የዳዊት መንግሥት ዋና ከተማ ከመሆኗ የተነሣ፣ እንዲሁም የመቅደሱ ቋሚ ስፍራ፣ እሷ ልዩ የተጽዕኖ ስፍራ አላት፣ በብኪ።

ሆኖም፣ እኔ እንደማስበው አኪ ለእስራኤል የተሰጡትን ብሔራዊ ተስፋዎች ሁለንተናዊ አድርጓቸዋል፣ ሰዎችን ሁሉ ለማካተት። መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት ከእንግዲህ ወዲያ የኢየሩሳሌም መቅደስ አይደለም፣ ነገር ግን አዲሱና የሚልቀው መቅደስ እንጂ፣ በኢየሱስ (የዕብራውያን መጽሐፍን ተመልከት)። ኢየሱስም ሆነ ወይም ሌላ ሐዋርያ ብሔራዊውን፣ መልክዓ-ምድራዊውን ተስፋ ለእስራኤል ፈጽሞ አላጸናም። ይህ የተለየ እንደሆነ አውቃለሁ፣ ካነበባችሁት/ከሰማችሁት፣ ከብዙ ደራስያን/ሰባክያን፣ ሴሚናሪዎች። የሚከተሉትን ልዩ ርዕሶች ተመልከቱ ይሄንን ሥነ-መለኮታዊ ማስረገጫ ከመተዋችሁ (ካለመቀበላችሁ) በፊት።

1. ልዩ ርዕስ፡ የብኪ ኪዳን ተስፋዎች ከአኪ ኪዳን ተስፋዎች እጅግ የተለዩ የሚመስሉት ለምንድነው?
2. ልዩ ርዕስ፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ

**122፡6 "ሰላም"** ቃሉ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰላም [ሻሎም])፣ "ሰላም" (ቢ.ዲ.ቢ. 1022) "ኢየሩሳሌም" የሚለውን ስም ክፋይ ይመሠርታል። የመቅደሱ ስፍራ የሞሪያ ተራራ እንደነበረ አስታውስ (ዘፍጥረት 22)። ዘፍጥረት 14 ላይ "ሳሌም" ተብሎ ተጠርቷል። እነዚህ የቃላት መቀያየሮች እጅግ ሥርወ-ቃላዊ አይደሉም፣ እንደ ድምጽ መቀያየሮች፣ በዕብራይስጥ፣ ነገር ግን ቃላቱ ዕብራይስጥ አይደሉም።

መዝ. 122፡6 ላይ ያሉትን የድምጽ መቀያየሮች ቁጥር ተገንዘብ።

1. መጸለይ – שאל (ቢ.ዲ.ቢ. 981፣ ኬቢ. 1371)
2. ሰላም – שלום (ቢ.ዲ.ቢ. 1022)
3. ኢየሩሳሌም –ירו שלם ( (ቢ.ዲ.ቢ. 436)
4. ብልጽግና – שלה (ቢ.ዲ.ቢ. 1017፣ ኬቢ. 1503)

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ከየትኛው የእስራኤል ዘመን ታሪክ ጋር ነው ይህ መዝሙር የሚዛመደው?
2. መዝ. 122፡5 ከ2 ሳሙኤል 7 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
3. ክርስቲያኖች አሁንም ለኢየሩሳሌም ሰላምና ብልጽግና መጸለይ ይኖርባቸዋልን?

# መዝሙር 123
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ለእግዚአብሔር እርዳታ ጸሎት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የመዓርግ መዝሙር | ከጥላቻ ለማረፍ ጸሎት | ከጠላቶች ለመታደግ ጸሎት (ሰቆቃ) | ጸሎት ለምሕረት | ጸሎት በጭንቀት ጊዜ |
| 123:1-2 | 123:1-2 | 123:1-2 | 123:1-2 | 123:1-2ለ |
| | | | | 123:2ሐ-ረ |
| 123:3-4 | 123:3-4 | 123:3-4 | 123:3-4 | 123:3-4ለ |
| | | | | 123:4ሐ |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (**ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል**)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 123፡1-2**
[1]**በሰማይ የምትኖር ሆይ፥**
**ዓይኖቼን ወደ አንተ አነሣሁ።**
[2]**እነሆ፥ የባሪያዎች ዓይኖች ወደ ጌታቸው እጅ እንደ ሆኑ፥**
**የባሪያይቱም ዓይን ወደ እመቤትዋ እጅ እንደ ሆነ፥**
**እንዲሁ እስኪምረን ድረስ**
**ዓይናችን ወደ አምላካችን ወደ እግዚአብሔር ነው።**

**123፡1** ይህ ከመዝ. 121፡1 ጋር ተመሳሳይ ነው (ዓይንን ወደ ላይ ማንሣት የጸሎት የአካል ምልክት ነው። መዝ. 121፡2 ላይ "ሰማይ" የሚያመለክተው ከምድር በላይ ያለውን ከባቢ አየር ነው (ዘፍ. 1፡1)፣ ነገር ግን እዚህጋ የእግዚአብሔርን ዙፋን ነው (መዝ. 11:4፤103:19፤ኢሳ. 66:1)። ልዩ ርዕሶች ተመልከት

1. ልዩ ርዕስ፡ ሰማይ
2. ልዩ ርዕስ፡ ሰማይ እና ሦስተኛው ሰማይ

በመዝሙር ላይ እንደተለመደው ሁሉ፣ በግለሰብ (ተናጠላዊ) እና በአጠቃላይ ላይ ተለዋዋጭነት አለ። ይህ መዝሙር "እኔ" ብሎ ይጀምራል፣ ግን ወዲያውኑ "እኛ" ወደሚል ያመራል።

**123፡2** "እጅ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 388፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ) ከላይ ላለ ሥልጣን ፈሊጥ ነው (ማለትም፣ ጌታ፣ እመቤት)። ያህዌ የመዳረሻው የሥልጣንና የጌትነት ምንጭ ነው። የእርሱ ሕዝቦች እሱን ይመለከታሉ።

▣ **"አምላካችን እግዚአብሔር"** ይህ በመጀመሪያ ዘፍ. 2፡4 ላይ ጥቅም ላይ ከዋለው መጠሪያ ጋር ተመሳሳይ ነው፣ እሱም ያህዌንና ኤሎሂምን የሚያደባልቅ። *ኤሎሀ* ነጠላ ቁጥር ዓይነት ሊሆን ይችላል። ይህ ሁለት መጠሪያ የእስራኤልን አምላክ ሁለት ባሕርያት ያደባልቃል።

1. *ፈጣሪ፣ ደጋፊ፣ መጋቢ ለሕይወት ሁሉ በዚህ ዓለም ላይ — ኤሎሂም*

2. አዳኝ፣ ኪዳን አድራጊ አምላክ — ያህዌ

▣ **"እንዲሁ እስኪምረን ድረስ"** የመዝሙረኛው ሁኔታ መዝ. 123፥3-4 ላይ ተገልጿል። እሱ በትዕግሥት ይጠባበቃል፣ እግዚአብሔር ከእርሱ አኳያ እስኪሠራ ድረስ (ቃል ያልተጠናቀቀ)። እሱም እግዚአብሔርን በጸሎት ሁለቴ ይጠራል፣ መዝ. 123፥3 (ሁለት ቃል ተተኳሪ) በእርሱ አኳያ እንዲሠራ፣ በርኅራኄና በምሕረት (ቢዲቢ 335፣ ኬቢ 334)።

**መዝሙር ፡ 123፥3-4**

**3 ማረን፥ አቤቱ፥ ማረን**
**ንቀትን እጅግ ጠግበናልና**
**4 የባለጠጎች ስድብና**
**የትዕቢተኞችን ንቀት**
**ነፍሳችን እጅግ ጠገበች።**

**123፥3ለ-4** በመዝሙር ላይ ተዘውትሮ እንደሚሆነው ደራሲው እንደተጠቃ ተሰምቶታል (እዚህጋ እሱ ደግሞ የሚገልጸው የተጠቃለለውን ገጽታ ነው)። እዚህጋ ባለጠጋ፣ ኃይለኛ እስራኤላዊ ሰዎች (ማለትም፣ ኢሳ. 32፥11፤ አሞጽ 6፥1)። የእነርሱ ድርጊት "በመጠላት" (ቢዲቢ 100) እና "በማፌዝ" (ቢዲቢ 541) ስሜት ሞልቶታል። በርግጠኝነት ማለት የሚቻለው መዝሙር 122 እና 123 የሚንጸባርቀው የዕዝራንና የነህምያን ጊዜ ነው። ዘወትር እንዲህ ዓይነት ሰዎች የሚያደርጉት ጌቶች እንደሆኑ ነው ነገር ግን መዝሙረኛው ያውቃል ያህዌ እውነተኛና የመዳረሻ ጌታ መሆኑን። ሕይወት ዘወትር ፍትሐዊ አይደለም፣ እናም የትዕግሥት ጸሎትና ተገቢ ርዕዮተ-ዓለምን ይሻል!

ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 1059) የሚያስረግጠው "የቁጥር 3-4 ቋንቋ የሚያመለክተው ጠላቶች ባዕዳን መሆናቸውን ነው፣ የእስራኤል ሰዎች ሳይሆኑ።" እኔ ግን መዝ. 123፥3-4 ላይ ምንም ነገር አላየሁም፣ ይህንን የሚያረጋግጥ፣ እናም ድኅረ-ስደት ኢየሩሳሌም ከዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ጋር በተሻለ ይገጥማል።

# መዝሙር 124

## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጸሎት ከጠላቶች ለመታደግ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዓርግ መዝሙር | ጌታ የሕዝቡ መከታ | ለብሔራዊ ትድግና ምስጋና ማቅረብ | እግዚአብሔር የሕዝቡ ጠባቂ | የእስራኤል አዳኝ |
| 124:1-5 | 124:1-5 | 124:1-5 | 124:1<br>124:2-5 | 124:1-3 |
| 124:6-8 | 124:6-8 | 124:6-7<br>124:8 | 124:6-8 | 124:4-5<br>124:6-7<br>124:8 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)

*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 124፡1-5**

**1እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን**
**እስራኤል እንዲህ ይበል።**
**2እግዚአብሔር ከእኛ ጋር ባይሆን**
**ሰዎች በእኛ ላይ በተነሡ ጊዜ፥**
**3ቍጣቸውን በላያችን በነደደ ጊዜ፥**
**በዚያን ጊዜ ሕያዋን ሳለን በዋጡን ነበር**
**4በዚያን ጊዜ ውኃ ባሰጠመን ነበር፥**
**በነፍሳችንም ላይ ፈሳሽ ባለፈ ነበር**
**5በዚያን ጊዜ የጐርፍ ውኃ በነፍሳችን ላይ ባለፈ ነበር።**

**124፡1-5** ይህ የአምልኮ ደንብ አንጓ ነው፣ ከብሔረ እስራኤል ትድግና ጋር የተያያዘ፣ ከባዕድ ወራሪዎች። ትክክለኛው ታሪካዊ መቼት አልተመለከተም።

*መዝሙረኛው ኃይለኛ ምናባዊ ምስያን ይጠቀማል፣ የያህዌን ማዳን ለመግለጽ።*

1. እሱ ከእነርሱ አኳያ ነው፣ መዝ. 124፡2
2. ጠላት እስራኤልን ሊውጠው ነበር፣ መዝ. 124፡3ሀ
3. የጠላት ቁጣ በእስራኤል ላይ ነድዶ ነበር፣ መዝ. 124፡3ለ
4. ጠላት እንደ ጎርፍ እስራኤልን አጥለቅልቆት ነበር፣ መዝ. 124፡4-5

**124፡1 "እስራኤል እንዲህ ይበል"** ይህ ቃል ያልተጠናቀቀ ነው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ ምላሹም በብሔራዊ ድል በዓል ላይ ተጠቅሷል /መዝ. 129፡1/፡፡

**124፡3ሀ** ይህ “የመዋጥ” ምናባዊ ምስያ (ቢዲቢ 118፣ ኬቢ 134) የመጣው
1. ምድርን ሰውኛ /ዘይቤ/ በማድረግ (ማለትም፣ ሞት፣ ሲኦል፣ ዘጸ. 15:12) ዓመጸኞቹን ሌዋውያን የዋጠበት በምድረ-በዳ የመዞር ጊዜ (ዘኍ. 16:30፤32፤ዘዳ. 11:6)
2. የነጣቂ አውሬ ጥቃት (መዝ. 35:25፤ምሳ. 1:12፤አሞጽ 2:16)፤ይህም ተለይቶ መዝ. 124:6ለ ላይ ተቀምጧል

**124፡3ለ** የቁጣ ምስያ እንደ መንደድ በመጀመሪያ ጥቅም ላይ የዋለው ዘፍ. 39፡19 ላይ ነው፡፡ እሳት ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው
1. ለፍርድ
2. ለቁጣ
3. ለማጽጃ ነው

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እሳት፡፡

**124፡4-5** የውኃ/ጎርፍ ምናባዊ ምስያ እንደ ሕይወት ችግሮች በበኪ ተደጋጋሚ ነው (ማለትም፣ ኢዮብ 22:11፤38:34፤መዝ. 32:6፤66:12፤69:2፤ 144:7፤ኢሳ. 43:2፤ሰቆ. 3:54)፡፡ እሱም ለወረራ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ኢሳ. 8:7-8 እና ኤር. 51:34፣ እዚህ መዝሙር ላይ እንደሆነ ሁሉ፡፡ የጎርፍ ውኃ ምድሩን እንደሚሸፍነው፣ እንዲሁ ደግሞ ወራሪ ሠራዊት፡፡ ሌላው የተለመደው ዘይቤ፣ ለዚህ የአንበጣ ወረራ ነው /ማለትም፣ ኢዩኤል/፡፡

ውኃ የሰው ጠላት ሆኖ በታየበት ጊዜ ሁሉ፣ ያህዌ የውኃውን ቀውስ /ሁከት/ ድል ያደረገበት ጠቃሽ ይሆናል (መዝ. 29:3፤10፤74:12-17፤ 89:9-10፤93:3-4)፡፡ ይህ ጭብጥ በከፊል የያህዌን ፈጣሪነት ያሳያል (መዝ. 124:8)፡፡

**መዝሙር ፡ 124፡6-8**

**[6]ለጥርሳቸው ንክሻ ያላደረገን**
**እግዚአብሔር ይባረክ።**
**[7]ነፍሳችን እንደ ወፍ ከአዳኞች ወጥመድ አመለጠች።**
**ወጥመድ ተሰበረ እኛም አመለጥን።**
**[8]ረድኤታችን ሰማይንና ምድርን በሠራ**
**በእግዚአብሔር ስም ነው።**

**124፡6-8** እግዚአብሔር ይባረክ (ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ *ቃል ተገብሮ አንቀጽ*) ብሔረ እስራኤልን ስላዳነ፡፡ የማዳኑ ባሕርይም
1. ከነጣቂ አውሬ ማምለጥ (ማለትም፣ መዝ. 7:2)
2. ከወፍ አዳኝ/ወጥመድ አመለጥን (መዝ. 91:3፤119:110፤ምሳ. 6:5)

**124፡7ለ** አንዱ ሊደነቅ ይችላል፣ ይህ የቅኔ ስንኝ የወራሪው ሠራዊት ጥፋትን የሚገልጽ ከሆነ፡፡

**124፡8ሀ** ስሙ ግለሰቡን ይወክላል፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ “ስም” የያህዌ፡፡

**124፡8ለ** ይህ ስብስብ ሐረግ ነው (መዝ. 102:25፤121:2፤124:8፤134:3፤146:6) የእስራኤልን አምላክ የተለየነት የሚያስረግጥ፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት /አንድ አምላክ ማመን/

# መዝሙር 125
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር በሕዝቡ ዙሪያ ነው<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት የመዓርግ መዝሙር | ጌታ፣ የሕዝቡ ብርታት | ከብሔራዊ ጠላቶች ለመታደግ ጸሎት /ሰቆቃ/ | የእግዚአብሔር ሕዝብ ደኅንነት | እግዚአብሔር ታማኞቹን ይጠብቃል |
| 125:1-3<br>125:4-5 | 125:1-2<br>125:3<br>125:4<br>125:5ሀ-ሐ<br>125:5መ | 125:1-5 | 125:1-2<br>125:3-5b<br>125:5ሐ | 125:1-2<br>125:3<br>125:4<br>125:5ሀ-ለ<br>125:5ሐ |

## የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 125፡1-3**

**1በእግዚአብሔር የታመኑ**
**እንደማይታወክ ለዘላለም እንደሚኖር እንደ ጽዮን ተራራ ናቸው።**
**2ተራሮች በኢየሩሳሌም ዙሪያ እንደ ሆኑ፥**
**ከዛሬ ጀምሮ ለዘላለም**
**እግዚአብሔር በሕዝቡ ዙሪያ ነው።**
**3ጻድቃን እጃቸውን ወደ ክፋት እንዳይዘረጉ**
**የኃጥአን በትር በጻድቃን ዕጣ ላይ አይኖርም።**

**125:1ሀ "በእግዚአብሔር የታመኑ"** ይህ ቁልፍ ሁኔታ ነው፣ ለመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት፡፡ ጽንሰ-ሐሳቡ ተደጋጋሚ ነው፣ መዝሙር ላይ (ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120፣ መዝ. 9:10፤21:7፤22:4-5፤25:2፤26:1፤28:7፤32:10፤37:3፤40:4፤55:23፤56:4፣11፤62:8፤84:12፤91:2፤112:7፤115:9፣10፣11፤125:1፤143:8)፡፡ ዘወትር ተመሳሳይ ጽንሰ-ሐሳብ ይገለጻል፣ እንደ

1. በስሙ ማመን – መዝ. 33:21
2. በምሕረቱ መታመን – መዝ. 13:5፤52:8
3. በቃሉ ማመን – መዝ. 119:42
4. በማዳኑ ማመን – መዝ. 78:22

ሥነ-መለኮታዊው ተዛማጅ ቃል ለመታመን (ቢዲቢ 52) ልዩ ርዕስ ላይ ተብራርቷል፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ የግሪኩ አቻ ነጥብ ልዩ ርዕስ ላይ ተገልጿል፡ እምነት፣ ማመን፣ መታመን በአኪ፡፡

ለእውነተኛና ለበሰለ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት/መታመን በርካታ መሠረታዊ ይዘቶች መኖራቸውን ወደ ማመን ደርሻለሁ፡፡

1. ንስሐ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ንስሐ በብኪ/
2. እምነት/መታመን/ማመን
3. መታዘዝ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ/
4. ጽናት /ትዕግሥት/ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽናት/

**125፡1ለ** ሙሉውን ሥነ-መለኮታዊ ማስታወሻ እና ሁለቱን ልዩ ርዕሶች ለመመልከት፣ ስለ እነዚህ ተስፋዎች፣ ለብሔረ-እስራኤል፣ የእኔን ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 122፡6-9 ላይ፡፡

LXX ይህንን የቅኔ ሐረግ /መስመር/ ለያህዌ ይጠቅሰዋል /ማለትም፣ "በኢየሩሳሌም የሚኖር አይናወጥም"/ ባጠቃላይ ይህ የሚመጣው ከያህዌ መጠሪያ ነው፣ መዝ. 9፡11 ላይ፡፡

**125፡2** "የተራሮች" ምናባዊ ምስያ በብዙ መልኩ ጥቅም ላይ ውሏል (መዝ. 121፡1 ላይ ማስታወሻ ተመልከት)፡፡ እዚህጋ የሚያመለክተው ከወራሪዎች የሚያደርጉትን መጠጊያ ነው፡፡ ያህዌ የሕዝቡ ጋሻና ጠባቂ ነው!

▣ **"ዘላለም"** ቃሉ (ቢ.ዲ.ቢ. 761) መዝ. 125፡1 እና 2 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፡፡ እሱም በርካታ ፍችዎች አሉት ከኪዳን ታማኝነት ጋር በተያያዘ፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም /ኦላም/፡፡

**125፡3 "በትር"** ይህ (ቢ.ዲ.ቢ. 986) የንግሥና ዘይቤ ነው (ማለትም፣ ያህዌ እንደ ንጉሥ መዝ. 45፡6)፡፡ እሱ በቅድሚያ ጥቅም ላይ የዋለው በመሲሐዊ መልኩ ነው፣ ዘፍ. 49፡10 ላይ፣ ለወደፊቱ የይሁዳ፣ ዳዊታዊ ንጉሥ /2 ሳሙኤል 7/፡፡ እዚህጋ ያለው ተስፋ ምንም ዓይነት /1/ የባዕድ ንጉሥ /2/ ጣዖት አምላኪ የይሁዳ ንጉሥ በእግዚአብሔር ሕዝብ ላይ እንደማይዛ ነው፡፡ ይህ ተስፋ ሁኔታዊ መሆኑ ግልጽ ነው /ማለትም፣ መዝ. 125፡3ለ፣4/፡፡

የመዝሙር 125፡3 የጊዜ ቅንብብ ርግጠኝነት የለውም፡፡
1. አሁን ጠላት እስራኤልን ተቆጣጥሮታል /የአሁን ጊዜ/
2. ጠላት እስራኤልን ተቆጣጥሮ ነበር /ያለፈ ጊዜ/
3. ጠላት ፈጽሞ እስራኤልን አይቆጣርም /የወደፊት ጊዜ/

▣ **"የኃጥአን"** ይህ የሚያመለክተው
1. የባዕድ ጣዖት አምላኪ ገዥ
2. ጣዖት አምላኪ እስራኤላዊ ገዥ

እሱም ከያህዌ የኪዳን መስፈርቶች የሚያፈነግጠውን ያመለክታል፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በምድሩ ላይ አያርፍም"** |
| **አየተመቅ፣ ጀፒኤስኦኤ፣** | |
| **የተእመቅ** | **"ምድሩ ተከፋፍሎ ተሰጠ"** |
| **አእቅ** | **"ዘወትር በምድሩ ላይ አይገዙም"** |
| **አኢመቅ** | **"በርስቱ ላይ ለማረፍ አይመጡም"** |
| **LXX** | **"በርስቱ ላይ"** |

ዕብራይስጡ መስተጻምር እና ስም አለው /ቢ.ዲ.ቢ. 174/፣ ርስትን የሚገልጽ፡፡ ምስያው የመጣው ከኢያሱ ተግባር ነው /ማለትም፣ ኢያሱ 12-19/ የከነአንን ምድር በመለኮታዊ ምሪት ለዕብራውያን በዕጣ ሲያከፋፍል /መዝ. 16፡5/፡፡

▣ **"ጻድቅ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ፡፡

▣ **"እጆች"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ፡፡

## መዝሙር ፡ 125፡4-5

**4 አቤቱ፥ ለቸሮች ልባቸውም ለቀና**
**መልካምን አድርግ።**
**5 ወደ ጠማማነት የሚመለሱትን ግን**
**ዓመፃን ከሚሠሩት ጋር እግዚአብሔር ይወስዳቸዋል።**
**ሰላም በእስራኤል ላይ ይሁን።**

**125፡4 "መልካምን አድርግ"** ይህ ሂፊል ተተኳሪ ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 405፣ ኬቢ. 408)፡፡ እግዚአብሔር "መልካም" ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 373 II፣ መዝ. 86፡5፤ 100፡5፤106፡1) እናም የእርሱ ሰዎች እሱን ሊያንጸባርቁ ይገባል (ዘዳ. 8፡16)፡፡

ሁለቱም የዕብራይስጥ ቃላት ለ "መልካም" እዚህ ቁጥር ላይ ጥቅም ላይ ውለዋል፡፡

**125፡5** መዝ. 125፡4-5 የሁለት ዓይነት ሰዎች ባሕርይ እንደሚያሳይ ተገንዘብ ("ለእነርሱ. . .")፡፡ ይህም "ሁለቱ መንገዶች" በሚል ይታወቃል (ዘዳ. 30፡15፣19፤መዝ. 1፡1)፡፡ አንዱ ከእግዚአብሔር ጋር ያለው ግንኙነት፣ እሱ/እሷ ሕይወትን በሚኖሩበት መንገድ ይታያል (ማቴ. 7፡15-23)! የዘላለም ሕይወት የሚስተዋሉ ባሕርያት አሉት!

▣ ***"ጠማማ መንገዶች"*** ጠማማ መንገድ /ቢ.ዲ.ቢ 785 የጽድቅ መንገድ ቀጥተኛ ተቃራኒ ነው (መዝ. 5:8፤139:24፤143:10)፡፡
ሰዎች የተገለጹበት ትይዩ መንገዶችን ተገንዘብ፡፡

1. "መልካም የሆኑ"
2. "ልባቸው ቅን የሆነ"
3. "ወደ ጠማማ መንገዳቸው የሚመለሱ"
4. "በደልን የሚፈጽሙ"

▣ **"ሰላም በእስራኤል ላይ ይሁን።"** ሰላም ሊሆን የሚችለው በሚያምነው፣ በታማኙ፣ በጻድቁ እስራኤል ላይ ብቻ ነው፡፡ እኪ ላይ ይህ የሚመለከተው የኢየሱስ ክርስቶስን ተከታዮች ነው (ገላ. 6:16)፡፡ ደግሞም ሮሜ. 2:28-29፤9:6፤ገላ. 3:7፣29፤ፊሊ. 3:3 ተመልከት! ብኪ መተርጎም የሚኖርበት በሙሉው የኢየሱስ መገለጥና በአኪ በኩል ነው!

የሰላም አምላክ እና የሰላም አለቃ በእርሱ ለሚያምኑ ሰላምን ይመኛል! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰላም /ሻሎም/፡፡

# መዝሙር 126

## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጆት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ምስጋና ከግዞት በመመለስ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የመዓርግ መዝሙር | ወደ ጽዮን የደስታ መመለስ | ከብሔራዊ መከራ ለመታደግ ጸሎት | የመታደግ ጸሎት | ከስደት በመመለስ ዝማሬ |
| 126:1-3 | 126:1-3 | 126:1-3 | 126:1-3 | 126:1-2ለ |
| | | | | 126:2ሐ-3 |
| 126:4-6 | 126:4 | 126:4 | 126:4-5 | 126:4-5 |
| | 126:5-6 | 126:5-6 | 126:6 | 126:6 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 126፡1-3**
1 እግዚአብሔር የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ፥
እጅግ ደስተኞች ሆንን።
2 በዚያን ጊዜ አፋችን ደስታን፥
አንደበታችንም ሐሴትን ሞላ
በዚያን ጊዜ በአሕዛብ ዘንድ።
እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን አደረገላቸው ተባለ።
3 እግዚአብሔር ታላቅ ነገርን አደረገልን፥
ደስም አለን።

**126፡1-3** ይህ አንጓ የእስራኤላውያንን ስሜት በተቃርኖ ያስቀምጠዋል፣ ተይዞ ወደ ግዞት መሄድ እና በታላቅ ደስታ ወደ ይሁዳና ኢየሩሳሌም እና መቅደሱ መመለስን፡፡

ለተርጓሚዎች ችግር የሚሆነው የዕብራይስጥ ግሦች የጊዜ ይዘት አለመሸከማቸው ነው፣ ዐውደ-ጽሑፍ ብቻ ነው የሚወስነው ያለፈውን፣ የአሁኑን፣ ወይም የወደፊቱን! ስለዚህ፣ የመጀመሪያው ቁጥር የሚሆነው

1. ያለፈ ድርጊት ማጽኛ/ማረጋጫ
2. የወደፊቱ ድርጊት ተስፋ
3. ያለፈ ድርጊት፣ መዝ. 126፡1፤ ወደ ያህዌ መጸለይ፣ ዳግም እንዲያደርገው፣ መዝ. 126፡4

**126፡1 "መለሰ"** ይህ ግሣዊ (ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ አወቃቀር*) ሰፊ የፍቺ መስክ አለው፡፡ እሱም የተለመደ ቃል ነው፣ "ለንስሐ" ጥቅም ላይ የሚውል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ንስሐ በብኪ) ከመሠረታዊ ፍችው "መዞር" ወይም "መመለስ፡፡" እሱም ሁለተኛው ፍች ነው፣ በመዝ. 126፡1 ላይ ከሚካተተው (ጄፒኤስኦኤ፣ መዝ. 85፡1 ላይ በመመሥረት፣ "መመለስ" የሚል አለው፣ ደግሞም መዝ. 14፡7፤53፡6) ተመልከት፡፡

በርካቶቹ የ “መዓርግ መዝሙራት” የዕዝራ/ነህምያን ጊዜ ከማንጸባረቃቸው የተነሣ፣ /ማለትም፣ የሲረስ አዋጅ በ538 ቅ.ል.ክ./፣ ይህ መዝሙር ደግሞ የድኅረ-ስደት ጊዜን ያንጸባርቃል፡፡

ለሥነ-መለኮታዊ ማስታወሻ ያህል፣ ከግዞት/ስደት ነጻነታቸውን ማግኘታቸው፣ ወደ ያህዌ መመለሳቸውን ተከትሎታል፡፡

▣ **“ምርኮ”** ታሳቢ ዕርማት /ማስተካከያ/ ይኖራል /እዚህጋ እና መዝ. 126፡4 ላይ/ ጀፒኤስኦኤን ተከትሎ፣ “እግዚአብሔር የጽዮንን ምርኮ በመለሰ ጊዜ”/፡፡

1. ሲመልስ – תבישׁ (ቢዲቢ 1000 II)፣ ኤምቲ

2. ሲመልስ – תובשׁ (ቢዲቢ 986)፣ ጀፒኤስኦኤ፣ መዝ. 85፡1

“ጻጋ” ሊያመለክት የሚችለው ብልጽግናን ነው (አእቅ የግርጌ ማስታወሻ)፡፡ እሱም ከያህዌ ጋር ያለው ኪዳን መመለስ የሚታይ ምልክት ነው፣ እንዲሁም የእርሱ የተስፋ በረከቶች (ሌዋውያን 26፤ዘዳግም 27-30)፡፡

▣ **“ጽዮን”** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽዮን፡፡

▣ ***“እጅግ ደስተኞች ሆንን”*** ይህ ከበርካታ ገላጭ ሐረጎች መካከል አንዱ ነው፣ የተመለሱትን ሰዎች ደስታ የሚገልጽ፡፡

1. መዝ. 126፡1ለ
2. መዝ. 126:2ሀ
3. መዝ. 126:2ለ
4. መዝ. 126:2ሐ-መ
5. መዝ. 126:3

እነዚህ ስሜቶች ከያህዌ ጋር ባለው ግንኙነት የተገኙ ውጤቶች ናቸው፡፡

ሙባጥ /ሙት ባሕር ጥቅሎች/ እና LXX “ሕልም” የሚለውን ቃል የሚመለከቱት םלח (ቢዲቢ 321 II) “ጤናማ፣” “ጠንካራ” የሚለውን ለማመልከት ነው (የተእመቅ)፤ሥሩ ፊደሉ የተዋቀረው በትክክል በተመሳሳይ ነው፡፡ ፔሺታ “እንደሚደሰቱ ሆንን” የሚል አለው፡፡

**126:2ሐ-መ “በአሕዛብ መካከል ተባለ”** ይህ ሐረግ ዳግም የሚያስረግጠው ማዕከላዊውን ሥነ-መለኮታዊ ማስረገጫ ነው፣ ማለትም፣ ያህዌ ከእስራኤል ጋር ያለውን ግንኙነት ወደ አሕዛብ ለመድረስ ለመጠቀሚያ መንገድነት እንደሚሻ /መዝ. 46፡10፤/፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ፡፡

***መዝሙር ፡ 126፡4-6***

**4አቤቱ፥ በደቡብ እንዳሉ ፈሳሾች**
**ምርኮአችንን መልስ።**
**5በልቅሶ የሚዘሩ በደስታ ይለቅማሉ።**
**6በሄዱ ጊዜ፥ ዘራቸውን ተሸክመው እያለቀሱ ተሰማሩ**
**በተመለሱ ጊዜ ግን ነዶአቸውን ተሸክመው ደስ እያላቸው ይመጣሉ።**

**126:4ሀ** ይህ ተተኳሪ /ልክ እንደ መዝ. 126፡1ሀ ያልተወሰነ አወቃቀር/ ለመረዳት አስቸጋሪ ነው፡፡ መዝ. 126፡1 የሚያስረግጠው የግዞተኞችን መመለስ ከሆነ፣ መዝ. 126፡4 ስለምን ለእነርሱ መመለስ ጸሎት ይሆናል? በዚህን ምክንያት ነው ጀፒኤስኦኤ የመዝ. 85፡1 ሞዴል /ማሳያ/ የሚጠቀመው፣ የብልጽግናን መመለስ መጥቀሱን ለማስረገጥ፡፡

**126፡4ለ** ይህ መልክዓ-ምድራዊ ዘይቤ ነው፣ ከበረሀ የውኃ ቦዮች ጋር የተያያዘ /ማለትም፣ ኔጌቭ/ ዋዲስ ተብሎ የሚጠራው፡፡ እነዚህ በውኃ መሞላታቸው ምናባዊ ምስያነቱ ለወደፊቱ የግብርና ምርት መትረፍረፍ ታላቅ በረከት ነው /ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30/፡፡

**126፡5-6** የተትረፈረፈ ውኃ ተስፋ፣ መዝ. 126፡4ለ ላይ ያለው እስከ ሌሎቹ የግብርና ፈሊጦች ይስፋፋል፡፡ “ዕንባ” /ቢዲቢ 199/ የሚያመለክተው

1. የደስታ ዕንባ በኪዳኑ መመለስ /ማለትም፣ የእስራኤል ወተትና ማር ወደምታፈስሰው ምድር መመለስ/
2. የእስራኤል ንስሐ ውጤት

**126፡6** ሁለት ዓይነት የተጠናከሩ ሰዋሰዋዊ ምሳሌዎች እዚህ ቁጥርጋ አሉ፡፡ ሁለት ጊዜ ያልተወሰነ የተጠናቀቀ እና ያልተጠናቀቀ ግሥ፣ የእንድ የዕብራይስጥ ሥር ጥቅም ላይ ውሏል፡፡

1. ወደ ፊትና ወደ ኋላ የሚሄድ – ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246
2. በርግጥ በድጋሚ ይመጣል – ቢዲቢ 9፣ ኬቢ 112

በእምነት/በንስሐ የሚዘሩ በርግጠኝነት ያጭዳሉ (ዘዳ. 30፡1-10)!

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“የዘር ከረጢት”** |
| **አኪጀቅ፣ አየተመቅ** | **“ዘር መሸከም”** |
| **የተእቅ፣ አኢመቅ፣** | |
| **LXX** | **“ዘር መያዝ”** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | **“የዘር ከረጢት”** |

ይህ ቃል (ቢዲቢ 604 I) ኢዮብ 28፡18 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ “መሳብ” በሚለው መልኩ፣ እዚህም ከረጢትን በመያዣ ገመድ እንደ መያዝ፡፡ የግሡ መልክ ፍችው “መሳብ” ወይም “መጎተት” ማለት ነው /አሞጽ 9፡13፡፡

ቲንዳሌ የብኪ ተከታታይ ሐተታ /ኮሜንተሪ/ /ቅጽ 16፣ ገጽ 476/ የሚለው ግሡ መጎተትን እንደሚያመለክት ነው /ማለትም፣ ጎትቶ መያዝ/ ዘርን /ማለትም፣ በአንድ ፈር ላይ አንድ ጊዜ፣ በስፋት ከመዝራት ይልቅ/፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የዚህን መዝሙር ታሪካዊ መቼት ለማወቅ አስቸጋሪ የሚሆነው ለምንድነው?
2. መዝ. 126፡1 ከመዝ. 126፡4 ጋር እንዴት አድርጎ የሚቃረን ይመስላል?
3. የመዝ. 126፡2ሐ-መ ሥነ-መለኮታዊ አንድምታ ምንድነው?
4. “ኔጌቭ”ን ግለጽ፡፡
5. “ማልቀስ” የሚለው መዝ. 126፡5 ላይ ያለው አንድምታው ምንድነው?

# መዝሙር 127
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ብልጽግና የሚመጣው ከጌታ ነው <br> <u>ኤምቲ መግቢያ</u> <br> የሰሎሞን የመዓርግ መዝሙር | ከጌታ ጋር መሥራትና መበልጸግ | ዋስትና ያለው ቤትና ትልቅ ቤተሰብ የጌታ ስጦታ ናቸው <br> /የጥበብ መዝሙር/ | የእግዚአብሔርን መልካምነት በማመስገን | በእግዚአብሔር ጥበቃ መታመን |
| 127:1-2 | | | | |
| | 127:1-2 | 127:1-2 | 127:1-2 | 127:1 |
| | | | | 127:2 |
| 127:3-5 | | | | |
| | 127:3-5 | 127:3-5 | 127:3-5 | 127:3-4 |
| | | | | 127:5 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 127፡1-2**

**[1]እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ፥**
**ሠራተኞች በከንቱ ይደክማሉ**
**እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ፥**
**ጠባቂ በከንቱ ይተጋል።**
**[2]በማለዳ መገሥገሣችሁም ከንቱ ነው።**
**ለወዳጆቹ እንቅልፍን በሰጠ ጊዜ፥**
**እናንተ የመከራን እንጀራ የምትበሉ፥**
**ከተቀመጣችሁበት ተነሡ።**

**127፡1-2** ይህ አንጓ የያህዌን ሉዓላዊነት ያስረግጣል፡፡ እሱ የሚሻው የተጠበቀ ነው! ያህዌ ለእስራኤል ሥነ-መለኮታዊ፣ ሁለንተናዊ ዓላማ ነበረው፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላማዊ የመዋጀት ዕቅድ፡፡

"ቤት" የሚለው ቃል (መዝ. 127:1) እና "ወዳጆቹ" (መዝ. 127:2) ለብሔረ-እስራኤል ዘይቤዎች ናቸው፣ ያህዌ ለአባቶች ከገባላቸው ልዩ ተስፋ እየዳበረ የመጣ /ሁለቱም ምድርና ዘር፣ ማለትም፣ ዘፍጥረት 12፡1-3፡፡

ትይዩውን ተገንዘብ "እግዚአብሔር ቤትን ካልሠራ" ... እና "እግዚአብሔር ከተማን ካልጠበቀ" በሚለው መካከል ያለውን፡፡
ይህ አንጓ የተዋቀረው

1. ትይዩነት
2. የድምጽ መቀያየር /ጨዋታ/ (ש)
   ሀ. "በከንቱ፣" መዝ. 127:1 (ሁለቴ)፣ 2 – ቢ.ዲ.ቢ. 996 (ልዩ ርዕስ ተመልከት: ከንቱ፣ ባዶ፣ ምንምነት)
   ለ. ጠባቂዎች፣ መዝ. 127:1 – ቢ.ዲ.ቢ. 1036
   ሐ. ጠባቂ፣ መዝ. 127:1 – ቢ.ዲ.ቢ. 1036
   መ. መትጋት፣ መዝ. 127:1 – ቢ.ዲ.ቢ. 1052
   ሠ. በማለዳ መገሥገሥ፣ መዝ. 127:2 – ቢ.ዲ.ቢ. 1014

ረ. አምሽተው የሚተኙ፣ መዝ. 127:2 – ቢዲቢ 442፣ בשׁ
ሰ. መተኛት፣ መዝ. 127:2 – ቢዲቢ 446፣ שׁנא፣ እሱም እዚህጋ ብቻ የሚገኝ ብኪ ላይ (ኤቢ፣ ገጽ 225 የሚለው ይህ የሶርያ ወይም ኢትዮጵያ ቃል "ብልጽግና" ሊሆን ይችላል፣ ይኸውም ከዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ጋር የሚገጥም፣ ሆኖም፣ "መተኛት"ም ደግሞ ከዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ጋር ደኅና አድርጎ ይገጥማል/

**127፡2** የሰው ጥረት ያለ እግዚአብሔር ዋጋ የለውም፣ ውጤታማ አይሆንም፣ ጊዜያዊም ነው /ዮሐንስ 15፡5/፡፡
ሦስት አንቀጾች /ግሦች/ እና ሁለት ያልተወሰኑ አወቃቀሮች አሉ፣ ትይዩ ሐረጎችን የሚያበጁ፡፡
1. ማለዳ መነሣት
2. አምሽቶ መተኛት
3. የአድካሚ ሥራን እንጀራ መመገብ

አስገራሚ የሚሆነው ኤቢ /ገጽ 223/ ቁ. 3ን የሚመለከተው ጣዖት አምላኪነትን እንደሚጠቅስ ነው፣ እናም የሚጠቅሰውም /1/ የጄሮም ማስታወሻ /ጁክስታ ሄልራኦስ/ እንደ ደጋፊነት እና /2/ መዝ. 106፡36፤37 እና መዝ. 139፡24፣ እነርሱም ከተመሳሳይ መሠረታዊ ሥር የሆኑ (ቢዲቢ 780 I እና ቢዲቢ 781)፡፡ ሆኖም፣ የብርቱ ሥራው ሐሳብ የተሻለ ትይዩ ይመስላል ለቁ. 1 እና ቁ. 2 ለአድካሚው የሰው ጥረት፣ የተፈለገውን ውጤት ለማግኘት፡፡

▣ **"ወዳጆቹ"** ይህ የሚመለከተው እስራኤልን ነው (ዘዳ. 33:12፤መዝ. 60:5፤108:6፤ኢሳ. 5:1፤ኤር. 11:14፤12:7)፡፡ ኤምቲ እና ሙባጥ /ሙት ባሕር ጥቅሎች/ "ሰሎሞን" የሚል ከመያዛቸው የተነሣ፣ አንዳንድ ሊቃውንት ከ2 ሳሙ. 12፡25 ጋር ያያይዙታል፣ እዚያም ሰሎሞን "ይዲድያ" ተብሎ የተጠራበት /ማለትም፣ በያህ የተወደደ/ በናታን።

**መዝሙር ፡ 127፡3-5**

**3እነሆ፥ ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታ ናቸው፥**
**የሆድም ፍሬ የእርሱ ዋጋ ነው።**
**4በኃያል እጅ እንዳሉ ፍላጾች፥**
**የጐልማስነት ልጆች እንዲሁ ናቸው።**
**5ከእነርሱ ዘንድ ምኞቱን የሚፈጽም ብፁዕ ሰው ነው**
**ጠላቶቻቸውን በአደባባይ በተናገሩ ጊዜ**
**እርሱ አያፍርም።**

**127፡3-5** ይህ አንጓ በመጀመሪያ ከመዝ. 127፡1-2 ጋር የሚዛመድ አይመስልም፣ ነገር ግን የመዝሙሩ ግፊት ባጠቃላይ የእግዚአብሔር ንቁ የሆነ ተሳትፎ ነው፣ በብሔረ-እስራኤል ሕይወት ላይ፡፡ ይህ መዝሙር የተመለከተው ለወቅቱ ንጉሥ ነው፡፡ ሕዝብ ብርቱ የሚሆነው እንደ ቤተሰቡ መዋቅር ነው፡፡

ጤነኛ ልጆች "የበረከቱ" አካል ምድብ ናቸው፣ በሁለቱም በሌዋ. 26፡9 እና ዘዳ. 7፡13፤28፡4፤30፡5፡፡ እሱም የጤናማ ኪዳናዊ ግንኙነት ምልክት ነው፣ ከእግዚአብሔር ጋር፡፡ እሱ የሰው ልጆችን "ብዙና ተባዙ" ብሎ ያዘዘ መሆኑን አስታውስ (ዘፍ. 2:27-28፤9:1፣7)፡፡

**127፡3**

| | |
|---|---|
| **ኤአመመቅ፣ ኤእቅ፣** | |
| **የተእመቅ** | **"የእግዚአብሔር ስጦታ"** |
| **ኤኪጀቅ፣ ኤየተመቅ፣** | |
| **LXX** | **"የእግዚአብሔር ውርስ"** |
| **ኤኢመቅ** | **"የመውለድ መብት፣ ከያህዌ"** |
| **ጄፒኤስኦኤ** | **"የእግዚአብሔር ስጦታ"** |

ቃሉ (ቢዲቢ 635) በመሠረቱ ፍችው ውርስ ነው (ኒዶቲ፣ ቅጽ. 3፣ ገጽ 77) ወይም "ንብረት" "ውርስ"
1. የሰው ውርስ – ዘፍ. 31:14፤ዘኁ. 27:7፣8፣9፣10፣11፤36:3፣8፤መዝ. 37:18
2. የእስራኤል ውርስ – ዘዳ. 4:21፤15:4፤19:10፤20:16፤24:4፤25:19፤26:1፤ኢሳ. 54:17
3. ዕጣ ወይም ክፍል – ኢዮብ 20:29፤27:13፤31:2

ይህ መዝሙር እንደ ተደራጀ እውነት ሊተረጎም ይችላል
1. ለአንድ ግለሰብ /ቁ. 1 ከላይ/
2. ለእስራኤል ንጉሥ እና ብሎም ለሕዝቡ /ቁ. 2 ከላይ/

ቁ. 2 ይሄንን መዝሙር በተሻለ የሚገጥም ይመስለኛል፡፡

**127፡5** ይህ የቅኔ ስንኝ አጽንዖት የሚሰጠው ብርቱ የሆነው ሕዝብ /ወይም የነገድ ወገን/ ራሳቸውን መከላከል እንደሚችሉ ነው፣ ምክንያቱም
1. ስለ አምላካቸው
2. ስለ እግዚአብሔር-ሰጥ ሕዝባቸው

ይህ የዳዊታዊ ንጉሥ ሥርወ-መንግሥት ደኅንነት ማጣቀሻ ሊሆን ይችላል /2 ሳሙኤል 7/፡፡

▣ **"እነርሱ አያፍሩም"** በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የንጉሡ ሥርወ-መንግሥታዊ ተስፋ፣ እንደሚመስለኝ "ማፈር" ወታደራዊ ሽንፈትን የሚያመለክት ነው፡፡ ለ "ማፈር" መዝ. 119፡6 ላይ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት፡፡

▣ **"በአደባባይ"** ይህ የሕግ፣ ንግድ፣ እና የማኅበራዊ ጉዳዮች ስፍራ ነው፡፡

ኤቢ /ገጽ 224/ ሌላ ሐሳብ ያቀርባል፣ ከዚህ የመጨረሻ የቅኔ ስንኝ ጋር በተያያዘ፡፡ መሠረታዊው የዕብራይስጥ ሐረግ ሊያመለክት የሚችለው የጦርነትን ትዕይንት ነው፣ ጠላት የተሸነፈበትን፡፡ ትርጉሙ የሚሆነው፣ "ነገር ግን ጠላቶቹን ከአደባባይ ያባርራቸዋል" ነው፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ወደ ማን ነው የተመለከተው?
2. "ወዳጆቹ" እነማናቸው፣ መዝ. 127፡2?
3. "ማፈር"ን ግለጽ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ፡፡
4. የቅኔው የመጨረሻ ስንኝን መረዳት የሚቻለው ከተመለከተለት /ከባለ አድራሻው/ አኳያ ነው፣ ለምን?

# መዝሙር 128
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔርን የመፍራት በረከት <u>ኤምቲ መግቢያ</u> የመዓርግ መዝሙር | እግዚአብሔርን የሚፈሩ ባርኮታቸው | ትልቅና ባለጠጋ ቤተሰብ ለጌታ ከመሰጠት የሆነ ሽልማት ነው /የጥበብ መዝሙር/ | ለጌታ ከመታዘዝ የሆነ ሽልማት | የታማኝ ባርኮቶች |
| 128:1-4 | | 128:1-4 | 128:1 | |
| | 128:1 | | 128:2-4 | 128:1 |
| | 128:2-4 | | | 128:2-3 |
| 128:5-6 | | 128:5-6ሀ | 128:5-6 | 128:4-6 |
| | 128:5-6ሀ | 128:6 | | |
| | 128:6ለ | | | |

## የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 128፥1-4**

**[1]እግዚአብሔርን የሚፈሩት ሁሉ፥**
**በመንገዶቹም የሚሄዱ ምስጉኖች ናቸው።**
**[2]የድካምህንም ፍሬ ትመገባለህ**
**ምስጉን ነህ መልካምም ይሆንልሃል።**
**[3]ሚስትህ በቤትህ እልፍኝ ውስጥ**
**እንደሚያፈራ ወይን ናት**
**ልጆችህ በማዕድህ ዙሪያ**
**እንደ ወይራ ቡቃያ ናቸው።**
**[4]እነሆ፥ እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው**
**እንዲህ ይባረካል።**

**128፥1 "የተባረከ"** ስለዚህ ቃል ማስታወሻ ተመልከት (ቢ.ዲ.ቢ 80) መዝ. 1፡1 ላይ፡፡ ሁለት ዓይነት ዋነኛ ቃላት አሉ፣ በዕብራይስጥ "የተባረከ" ወይም "ደስተኛ፣" ለሚሉት ጽንሰ-ሐሳቦች፣ ሁለቱም ከእግዚአብሔርና ከሰው ጋር በተያያዘ፡፡ ዘዳግም 33ን እንደ ምሳሌ ልጠቀም

1. የተባረከ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ባርኮት [OT])
   ሀ. ስም – ቢ.ዲ.ቢ 139፣ ዘዳ. 33፡1፣11
   ለ. ግሥ – ቢ.ዲ.ቢ 138፣ ዘዳ. 33፡1፣13፣20፣24
2. የተባረከ – ቢ.ዲ.ቢ. 80፣ መዝ. 1፡1 እና 18 ላይ ጥቅም ላይ የዋለ ብዙ ጊዜ መዝሙር ላይ፣ ነገር ግን ዘፍጥረት ወይም ዘዳግም ላይ ሳይሆን

የያህዌ ባርኮቶች በቀጥታ የሚገናኙት በኪዳኑ ከተሸፈኑት ጋር ነው፡፡ እሱም የተመሠረተው በመታዘዝ ነው /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መጠበቅ/፡፡ ይህ የብልጽግናና የይዞት ሙሉ ጽንሰ-ሐሳብ የብኪ "ሁለቱ መንገዶች" ክፍል ነው፣ መዝሙር 1፤ ዘዳ. 30፡15፣19 ላይ የሚታይ፣ እንዲሁም "ርግማን" እና "በረከት" ሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30 ላይ ተገልጸዋል፡፡

በትክክል የተባረከ ሰው ግንኙነቱ በአግባቡ የሆነ ነው /1/ ከእግዚአብሔር ጋር /2/ ከቤተሰቡ/ከቤተሰቧ፣ እና /3/ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር፡፡ ሦስቱም ንፍቀ-ክበቦች ሁሉ በኅብር መሆን አለባቸው!

▣ **"እያንዳንዱ"** ይህ እንዴት እንደተወሰነ ተገንዘብ፡፡

1. እግዚአብሔርን የሚፈሩ እነርሱ፣ መዝ. 128:3፤4 (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፍርሃት [ብኪ])
2. በመንገዶቹ የሚሄዱ እነርሱ (መዝ. 119:2-3)

ስለዚህ በረከቱ "ለእያንዳንዱ" አይደለም፣ ለኪዳኑ ሕዝብ እንኳ ቢሆን፣ ነገር ግን ለታማኝ ተከታዮች ብቻ እንጂ!

ይህም የሚኖረው አንድምታ ክርስቲያኖች አዲሱን የእስራኤል መንግሥት /ሕዝብ/ እንዴት እንደሚመለከቱ ነው፡፡ የኪዳን ታዛዥነት ለኪዳን ተስፋዎች ቀዳሚ መስፈርት ነው!

▣ **"መንገዶች"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ለእግዚአብሔር ራዕይ /መገለጥ/ ቃላት

**128፡2-3** የታማኝ ተከታዮችን የኪዳን ተስፋዎች ተገንዘብ /እዚህ፣ ለአንድ ግለሰብ ነው/፡፡

1. የድካማቸውን ፍሬ ይመገባሉ
2. ይደሰታሉ
3. መልካም ሕይወት
4. መልካም የትዳር ሕይወት
5. ብዙ ጤነኛ ልጆች
6. ረጅም ዕድሜ

ይህ የብኪ ባርኮቶች ይዘት ነው፡፡ ያህዌ የአሕዛብን ትኩረት ለመማረክ ፈልጓል፣ እስራኤልን በመባረክ፡፡ አንዴ እንዲገነዘቡ፣ እስራኤል የበረከታቸውንና የሰላማቸውን ምንጭ እንደሚካፈል - ያህዌን፡፡

*መቀመጥ ያለበት፣ የበዛ የሕዝብ እድገት የእግዚአብሔር ትዕዛዝ መሆኑ ነው*

1. ዘፍ. 1:28፤9:1፤7
2. እሱም የአብርሃም በረከት ክፋይ ነው፣ ዘፍ. 12:2፤13:16፤16:10 ላይ
3. እሱም ደግሞ የያዕቆብ ቤተሰብ እውነታ ነው (ዘፍ. 28:14) ግብፅ ላይ ፣ ግብፃውያን መሪዎች እስራኤልን እንዲፈሩና እንዲያሣቀዩ ያስደረጋቸው (ዘጸአት 1-2)፡፡

**128፡2ሀ** ማስታወሻ ለመጥቀስ ያህል ይህ ተስፋ የግዞት ሥቃይ ቀጥተኛ ተቃራኒ ነው! ግዞቶች የእግዚአብሔር ፍርዶች ነበሩ በእምነተ-ቢስ የኪዳን ተከታዮች፡፡ ይህም እጅግ ተቃራኒው ነው፣ እሱ ካሰበው ዓላማ አኳያ፡፡ እሱ ውስጠ-ወይራ አባባል ነው፡፡

**መዝሙር ፡ 128፡5-6**

**[5]እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ**
**በሕይወትህ ዘመን ሁሉ፥ የኢየሩሳሌምን መልካምነትዋን ታያለህ።**
**[6]የልጆችህንም ልጆች ታያለህ።**
**በእስራኤል ላይ ሰላም ይሁን።**

**128፡5-6** ይህ የመዝጊያ ጸሎት ነው፣ ለሁለቱም፣ ለግለሰብ ታማኝ ተከታይ እና ለብሔረ-እስራኤል /መዝ. 128፡6ለ/፡፡

1. መዝ. 128:5ሀ – ይባርክህ (ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ ፒኤል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ)
2. መዝ. 128:5ለ – ታያለህ. . . (ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ ቃል ተተኳሪ)
3. መዝ. 128:6ሀ – እንደ ቁ. 2 ተመሳሳይ
4. መዝ. 128:6ለ – ግሥ የለውም ነገር ግን ጸሎት ይመስላል (መዝ. 125:5)

አስገራሚ የሚሆነው የጳውሎስ የቤተ-ክርስቲያን ጠቃሽ፣ ገላ. 6:16 ላይ ተመሳሳይ ሐረግ ነው የተጠቀመው፣ መዝ. 128:6፡፡ ቀጥተኛ፣ ንቁ /የታሰበበት/ ጠቃሽ ቢሆንም ርግጠኝነት የለውም፡፡

▣ "የኢየሩሳሌም ብልጽግና" ከ "የልጆችህን ልጆች ታያለህ" ጋር ትይዩ መሆኑን ተገንዘብ፡፡ ይህም የሚያመለክተው የረጅም ጊዜ ሰላም፣ ብልጽግና፣ እና የኅብረተሰቡን ጽኑዕነት ነው፡፡

**128:5 "ከጽዮን"** ይህ የሚያመለክተውየያህዌን ማደሪያ ነው፣ በመቅደስ (መዝ. 1234:3)፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽዮን፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. “የተባረከ” የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ግለጽ /መዝ. 128፥1ሀ/።
2. “ፍርሃት” የሚለውን የዕብራይስጥ ቃል ግለጽ /መዝ. 128፥1ሀ/።
3. “ብዙ ልጆች” ለምን እንደ በረከት ተቆጠረ?
4. የእምነት፣ ቤት፣ እና ሕዝብ ምድቦች እንዴት ሊያያዙ ቻሉ?

# መዝሙር 129
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
| --- | --- | --- | --- | --- |
| ጸሎት የጽዮንን ጠላቶች ለመጣል<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የመዓርግ መዝሙር | የድል ጸሎት በጽዮን ጠላቶች ላይ | ጸሎት ከብሔራዊ ጠላቶች ለመታደግ<br>/ሰቆቃ/ | ጸሎት በእስራኤል ጠላቶች ላይ | በእስራኤል ጠላቶች ላይ |
| 129፡1-4 | 129፡1-4 | 129፡1-8 | 129፡1-4 | 129፡1-2<br>129፡3-4 |
| 129፡5-8 | 129፡5-8 | | 129፡5-8 | 129፡5-8ለ<br>129፡8ሐ |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ ብሔራዊ ሰቆቃ ነው፡፡ "ወንድ ልጅ" ለሚለው ለእስራኤል አጠቃቀም፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር ልጅ፡፡

ለ. ሁለተኛው አንጓ /መዝ.129፡5-8/ በእስራኤል አሳዳጆች ላይ ርግማን ነው፣ እነርሱም ባጠቃላይ ባዕዳን የሆኑ፡፡

ሐ. አብዛኞቹ ምናባዊ ምስያዎች፣ የእስራኤልን ሕይወትና እምነት የሚጠቅሱት የተወሰዱት ከግብርና ነው፡፡ ዋነኛ ነገር የሚሆነው፣ የሚከተሉትን እውነቶች ማስታወሳችን ነው፣ መዝሙራትን ስንተረጉም፡፡
1. እነርሱ ብኪ ናቸው፣ አኪ ሳይሆኑ
2. እነርሱ ከጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/ መቼት ጋር ይዛመዳሉ
3. እነርሱ የሚያተኩሩት ከኪዳን ታዛዥነት እና በማዕከላዊነትም ከብሔረ እስራኤል ጋር ነው፣ በእግዚአብሔር ዕቅድ ላይ
4. እነርሱ መተርጎም የሚኖርባቸው ከአኪ ወንጌል አንጻር ነው

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 129፡1-4**

**[1]እስራኤል፡፡**
**ከትንሽነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ ተሰለፉብኝ ይበል**
**[2]ከትንሽነቴ ጀምሮ ብዙ ጊዜ ተሰለፉብኝ**
**ነገር ግን አላሸነፉኝም፡፡**
**[3]ኃጢአተኞች በጀርባዬ ላይ መቱኝ፥**
**ኃጢአታቸውንም አስረዘሙአት፡፡**
**[4]እግዚአብሔር ጻድቅ ነው**
**የኃጢአተኞችን አንገታቸውን ቈረጠ፡፡**

**129፡1-2** መዝሙር 129፡1፣ ስንኝ 1 በቅድሚያ የሚመስለው ታማኝ ግለሰብ ያለበትን ሁኔታ ማመልከት ነው፣ ነገር ግን የስንኝ 2 ግሥ (ቢዲቢ 55፣ ኬቢ 65፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ) የሚያመለክተው ይህ ብሔራዊ ሰቆቃ መሆኑን ነው፡፡ ይህ መዝሙር እስራኤል በየጊዜው ለምን መከራ እንደሚቀበል አያስቀምጥም፡፡ እንደ አብዛኞቹ መዝሙራት፣ የኪዳኑ ሕዝብ ኃጢአቱን መቀበሉ አልተገለጸም፣ ግን ይገመታል፡፡ የሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-28 አስፈሪ እውነታ ብሔራዊ እውነታ ሆኗል፡፡

**129፡2ለ** ብሔረ-እስራኤል በሕልውና ሊቆይ የቻለው ከምሕረት የተነሣ ነው /ሚልክያስ 1/ እና ከእግዚአብሔር ዓላማ አኳያ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ/፡፡

**129፡3** ይህ የግብርና ምናባዊ ምስያ የሚገልጸው መከራ እና ሥቃይን ነው፡፡

**129፡4ሀ** እስራኤሎች ሊኖሩ የቻሉት ከአምላካቸው የተነሣ ነው፡፡ እሱ ለባሕርዩ እውነት ነው /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ/ እና ለዓላማው (ዘፍ. 3:15፤ዘጸ. 19:5-6፤ኢሳ. 2:2-4፤ሚክ. 4:1-3)፡፡

**129፡4ለ** ይህ ("ገመድ፣" ቢዲቢ 721) የሚያመለክተው

1. የእንስሳት ወጥመድ (መዝ. 140:5)
2. የበሬ ቀንበር ማሰሪያ (ኢዮብ 39:10)
3. የእስረኛ ማሰሪያ

ኤቢ /ገጽ 231/ የሚለው ይህን የቅኔ ስንኝ መገንዘብ የሚገባው እንደ ተጽዕኗዊ ነው /እንደ መዝ. 129፡5-6/፣ እሱም ጸሎትን የሚጠቅስ፡፡ ያህዌ ቀደም ብሎ "ከቆረጠው" (ቢዲቢ 893፣ ኬቢ 1125፣ ፒል የተጠናቀቀ)፣ የመዝ. 129:5-6 ርግማን ለምን? ዳሆድ እሱን ልመና የተጠናቀቀ ያደርገዋል፣ ይኸውም ከተጽዕኗዊ ጋር በትይዩነት እንደሚገኝ በማመልከት፡፡ ይህ እውነት ከሆነ፣ እንግዲያውስ መዝ. 129፡4 አዲስ አንጓ ይጀምራል (ማለትም፣ መዝ. 129:4-8)፣ ስለዚህ፣ "ያህዌ ገመዶቹን ይቁረጥ /ማለትም፣ የበሬ ማረሻ/ የኃጢአተኞችን" እንደሚለው ትርጉም ያለ፡፡ አብዛኞቹ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች (አኪጀቅ፣ አየተመቅ፣ አእቅ፣ አኢመቅ፣ ጄፒኤስኦኤ፣ የተእመቅ) ግሡን የሚተረጉሙት እንዳለፈ ሁነት ነው፡፡

**129፡4-8** ይህ አንጓ የሚገልጸው ጽዮንን በሚጠሉ ላይ የሚሆነውን ርግማን ነው /ማለትም፣ ፍችውም ያህዌንና የእርሱን ሕዝብ/፡፡ በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ፣ ጽዮን የሚጠቅሰው ብሔረ-እስራኤልን ነው፣ በእርሱ መካከልም የኢየሩሳሌም ቤተ-መቅደስ እንደሚሆን፡፡

1. ይፈሩ – ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 129:5
2. ወደ ኋላቸው ይመለሱ – ቢዲቢ 690፣ ኬቢ 744፣ *ኒፋል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 129:6
3. በሠገነት ላይ እንዳለ ሣር ይሁኑ – ቢዲቢ 224፣ ኬቢ 243፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ፣ መዝ. 129:6
   ሀ. ሳያድግ እንደሚጠወልግ፣ መዝ. 129:6ለ
   ለ. አጫጁ ምንም ፍሬ የማያገኝበት፣ መዝ. 129:7
4. ማንም የማይባርካቸው፣ መዝ. 129:8

***መዝሙር ፡ 129፡5-8***

**5 ጽዮንን የሚጠሉ ሁሉ**
**ይፈሩ፥ ወደ ኋላቸውም ይመለሱ።**
**6 በሰገነት ላይ እንደ በቀለ ሣር፥**
**ሳይነቀል እንደሚደርቅ፥**
**7 ለሚያጭደው እጁን፥**
**ነዶዎቹን ለሚሰበስብ እቅፉን እንደማይሞላ ይሁኑ።**
**8 በመንገዱም የሚያልፉ።**
**የእግዚአብሔር በረከት በእናንተ ላይ ይሁን**
**በእግዚአብሔር ስም እንመርቃችኋለን አይሉም።**

**129፡5ለ "ይፈሩ"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 101፣ ኬቢ 116) የሚገልጸው ከያህዌ ጋር ካለ ኅብረት የወጣ እና በእርሱ ፍርድ ሥር ያለ ሰውን ነው፡፡ እሱም ጥቅም ላይ የዋለው

1. ለባዕዳን
2. ለዓመጸኛ እስራኤላውያን

እሱም የሚጠቅሰው ታማኝ ያለመሆንን ወይም ያለማመንን መዘዝ ነው፣ ሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30 ላይ የተጠቀሰውን፣ ተጨባጭ እንደሆነ (ኒዶቲ፣ ቅጽ 1፣ ገጽ 621-627 ተመልከት)፡፡ ለ"ማፈር" መዝ. 119:6 ላይ ማስታወሻ ተመልከት፡፡

**129፡8ሀ-ለ** ይህ የሚያመለክተው ባርኮትን ነው፣ ባልንጀሮች፣ ቤተሰብ፣ እና ጎረቤቶች ለባለ አዝመራዎች የሚያቀርቡት ነው /ሩት 2፡4/፡፡

**129፡8ሐ** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የዚህ መዝሙር መክፈቻ የአምልኮ ሥርዓትን ያመለክታልን?
2. እስራኤል ለምን "ወጣት" ተባለ?
3. "ገመዶች" የሚጠቅሱት ምንድነው፣ መዝ. 129፡4 ላይ?
4. "እፍረትን" ግለጽ፡፡
5. የመዝ. 129፡8 ታሳቢ ታሪካዊ መቼት ምንድነው?

# መዝሙር 130
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| በጌታ የምሕረት ፍቅር ተስፋ ማድረግ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የመዓርግ መዝሙር | የጌታን መቤዠት መጠበቅ | ጸሎት ከግል ችግር ለመዳን | የዕርዳታ ጸሎት | ከጥልቁ መውጣት |
| | 130:1-2 | | | |
| 130:1-4 | 130:3-4 | 130:1-2 | 130:1-4 | 130:1-2 |
| | 130:5-6 | 130:3-4 | | 130:3-4 |
| 130:5-8 | 130:7-8 | 130:5-6 | 130:5-6 | 130:5-7ሀ |
| | | 130:7-8 | 130:7-8 | 130:7ለ-8 |

## የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ ከመዝሙራቱ መካከል አንዱ ነው፣ ስለ ታማኝ ተከታዮች ጥልቅ መሻትና ተስፋዎች የሚናገር፡፡
1. ችግሮች፣ ኃጢአት፣ እና ቅር መሰኘቶች አሉ
2. አማኙ ይጮኻል ወደ እርሱ/እርሷ ብቸኛ ተስፋ፣ እግዚአብሔር
3. እሱ ይሰማል፣ ይቅርም ይላል
4. እሱ ታማኝ ነው፣ ለባሕርዩ እና ቃሉ፣ ሰዎች እንኳ ባይሆኑ /መዝ. 51፡1/

ለ. በርካታ ስሞች አሉ ለእስራኤል አምላክ መጠሪያ፣ በመዝሙሩ ጥቅም ላይ የዋሉ፡፡
1. ያህዌ፣ መዝ. 130:1፣5፣7 (ሁለቴ)
2. ያህ፣ መዝ. 130:3 (የያህዌ ምሕጻረ ቃል)
3. አዶን፣ መዝ. 130:3፣6

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፡፡

ሐ. ይህ መዝሙር ሁለቱንም የግለሰብንና የተጠቃለለን የመታደስን /መመለስን/ መናፈቅ ይገልጻል /መዝ. 130፡7-8/፡፡

መ. ሰዋሰዋዊ ሥነ-መለኮታዊ አጽንዖቱን ተገንዘብ፣ የመዝ. 130፡7-8ን፡፡
1. መዝ. 130፡7፣ "የተትረፈረፈ መዋጀት" (ቢዲቢ 915 I፣ ኬቢ 1176፣ ሂፊል ያልተወሰነ የተጠናቀቀ)
2. እሱ /እና እሱ ብቻ/ ነው የሚዋጀው — ሰዋዊ ተውላጠ ስም ግሡ ላይ ተጨምሯል፣ ለአጽንዖት

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 130፡1-4**

[1]አቤቱ፥ አንተን ከጥልቅ ጠራሁህ።

²አቤቱ፥ ድምፄን ስማ
ጆሮህ የልመናዬን ቃል
የሚያደምጥ ይሁን።
³አቤቱ፥ ኃጢአትንስ ብትጠባበቅ፥
አቤቱ፥ ማን ይቆማል?
⁴ይቅርታ ከአንተ ዘንድ ነውና።

**130:1 "ከጥልቅ"** ይህ ስም (ቢ.ዲ.ቢ. 771) በርካታ ዘይቤአዊ አጠቃቀሞች አሉት፡፡ የእሱም መሠረታዊ ፍች "ጥልቅ" ነው፡፡

1. መከራ እንደ ጎርፍ ውኃ ተገልጿል፣ መዝ. 69:1-2፤14-15 (ተመሳሳይ ዘይቤ እንደ መዝ. 42:7ሀ፤88:7)
2. ያህዌ የውኃውን ሁከት እንዳሸነፈ፣ ኢሳ. 51:9-10 (ከመዝ. 74:12-17፤89:9-10 ጋር ተመሳሳይ)
3. የጢሮስ ባሕር ኃይል ድል መሆን (ማለትም፣ ወደ ባሕር መስጠም)፣ ሕዝ. 27:34
4. የሲኦል ማጣቀሻ ሊሆን ይችላል፣ ዮናስ 2:2-6፤መዝ. 18:4-5)

▣ **"ወደ አንተ ጮኹኩ"** የመዝሙረኛው ርግጠኛ ጭንቀት አልተቀመጠም፣ ነገር ግን ከኃጢአተኝነት ስሜቱ ጋር የተያያዘ ይመስላል (መዝ. 130:3-4)፡፡ እሱ የተገለለ ይመስለዋል፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ንስሐ የገባና የታገሥ ተከታይን ይቅር እንደሚልና እንደሚመልስ አውቋል (መዝ. 130:5-6)!

**130:2** ይህ ቁጥር የሚያንጸባርቀው የመዝሙረኛውን ጸሎት ነው፣ መዝ. 130:1 ላይ የተጠቀሰውን፡፡

1. ስማ – ቢ.ዲ.ቢ. 1033፣ ኬቢ. 1570፣ ቃል ተተኳሪ
2. ጆሮችህም ያድምጡኝ – ቢ.ዲ.ቢ. 224፣ ኬቢ. 243፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

**130፡3-4** በርካታ የእንግሊዝኛ ትርጉሞች እነዚህን ሁለት ቁጥሮች የተነጣጠሉ አንጓዎች ያደርጓቸዋል (ማለትም፣ አኪጀቅ፣ አየተመቅ፣ አኢመቅ)፡፡
የሰዎች ሁሉ ኃጢአኝነት እውነታ፣ ከዘፍጥረት 3 ውድቀት በኋላ ተደጋጋሚ እውነት ነው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉ፡፡

1. ዘፍጥረት 3:17-19፤6:5፣11-12፤8:21
2. 1 ነገሥት 8:46
3. 2 ዜና መዋዕል 6:36
4. ዕዝራ 9:15
5. ኢዮብ 4:17፤9:2፤15:14-16፤25:4
6. መዝሙር 51:5፤76:7፤130:3፤143:2
7. ምሳሌ 20:9
8. መክብብ 7:20
9. ኢሳይያስ 53:6
10. ናሆም 1:6
11. ሚልክያስ 3:2
12. ሮሜ 3:9-18፣19፣23፤11:32
13. 1 ዮሐንስ 1:8-10
14. ራዕይ 6:17

ሁሉም ይቅርታ ያስፈልጋቸዋል! ሰዎች ይቅርታ እንደሚያስፈልገን አንገነዘብም፣ መንፈስ ቅዱስ በግልጽ እንደሚያስፈልገን እስካልገለጠልን ድረስ፡፡ ምንም አዳኝ አያስፈልግም፣ የመጥፋት ስሜት እስከሌለ ድረስ! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ይቅርታ በብኪ፡፡ ይቅርታ ይቻላል፣ ምክንያቱም

1. ከባለጸጋው፣ ከማይለወጠው ከእግዚአብሔር ባሕርይ የተነሣ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት [ብኪ])
2. ከተጠናቀቀው ከመሲሑ ሥራ የተነሣ (ኢሳይያስ 53፤ማርቆስ 10:45፤2 ቆሮ. 5:21)
3. ከመንፈስ ቅዱስ መሳብ፣ መቃተት የተነሣ (ዮሐንስ 6:44፣65፤16:8-15)

**130:3 "ምልክት"** ይህ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 1036፣ ኬቢ. 1581፣ ቃል ያልተጠናቀቀ) በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ የሚገልጸው፣ የመዝገብ መቀመጥን ነው፡፡ ይኸም በእግዚአብሔር "ሁለቱ መጻሕፍት" ይንጸባረቃል /ማለትም፣ ድርጊቶች/መታሰቢያዎች እና የሕይወት መጽሐፍ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር ሁለቱ መጻሕፍት/፡፡ ይህ ዘይቤ ነው ለእግዚአብሔር ማስታወስ፡፡

እሱ ውስጠ-ወይራ ነው፣ ነገር ግን እግዚአብሔር ደግሞ ደጋግሞ ይጠየቃል፣ ኃጢአታችንን እንዲረሳ (ማለትም፣ መዝ. 79:8፤106:6፤ኢሳ. 64:9፤ሚክያስ 7:18) ነገር ግን የተሰፋ ቃሉን ያስባል፡፡ በፍርድ ቀን መጻሕፍቱ ይከፈታሉ (ዳን. 7:10፤ራዕ. 20:12)!

**130:4 "መፍራት"** በመሐሪው አምላክ የተደረገ ነጻና ሙሉ ይቅርታ ውጤቱ ከእግዚአብሔር ጋር የሚሆን የግል ኅብረት መመለስ ነው /ማለትም፣ ዘፍጥረት 3 ውድቀት ላይ ጠፍቶ የነበረው/፣ እሱም የፍጥረት ግብ ነው/ነበር/ይሆናልም፡፡ እኛ የተፈጠርነው በእርሱ እና ለእርሱ ነው፡፡ ፍርሃት ተገቢ አክብሮት ነው፣ ለእርሱ የሚገባ፡፡ የምሕረት ውጤት በኅብረት ይታያል! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፍርሃት /ብኪ/፡፡

## መዝሙር ፡ 130፡5-8

⁵አቤቱ፥ ስለ ስምህ ተስፋ አደረግሁህ
ነፍሴ በሕግህ ታገሠች።
⁶ከማለዳው ሰዓት ጀምሮ
እስከ ሌሊት

ነፍሴ በእግዚአብሔር ታመነች።
[7]ከእግዚአብሔር ዘንድ ምሕረት፥
በእርሱም ዘንድ ብዙ ማዳን ነውና
እስራኤል በእግዚአብሔር ይታመን።
[8]እርሱም እስራኤልን
ከኃጢአቱ ሁሉ ያድነዋል።

**130፡5-8** ይህ አንጓ አጽንዖት የሚሰጠው ጭብጥ ታማኝ ተከታዮች በእግዚአብሔር እንደሚታገሡና በቃሉም እንደሚታመኑ ነው /መዝ. 130፡5/፡፡ “በእምነት መጠበቅ’ የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ እዚህ አንጓ ላይ በሁለት ቃላት ተገልጿል፡፡

1. ቢዲቢ 875፣ ኬቢ 1082 – መዝ. 130:5 (ሁለቴ) እና መዝ. 130:6፣ መዝ. 25:3፣21፤27:14፤40:1፤56:7 በታሳቢነት
2. ቢዲቢ 403፣ ኬቢ 407 – መዝ. 130:5፣7፣ መዝ. 38:15፤42:5፤43:5

ይህ የአምላክ ሉዓላዊነትና የወደቀው የሰው ልጅ የሚፈለግበት የፍቃደኝነት ምላሽ የሚገናኙበት ስፍራ ነው፡፡ ታማኝ ተከታዮች መጠበቅን፣ ተስፋ ማድረግን፣ በእግዚአብሔርና በእሱ ተስፋ መታመንን ይመርጣሉ፣ ምንም እንኳ ሁኔታዎችና ስሜት የተለየውን መንገድ ለመራመድ ቢጮኹም!

**130፡6** ይህ ይሆናል ብሎ የመጠበቅ ዘይቤ ተመሳሳይ ነው ከመዝ. 42፡1-2 ጋር፡፡ የእግዚአብሔር ሕዝቦች እሱን ይናፍቃሉ /ይጠብቃሉ/!

▣ **“ነፍስ”** ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት ዘፍ. 35፡18 ላይ www.freebiblecommentary.org በድረ-ገጽ መስመር፡፡

**130፡7** መዝሙረኛው ያህዌን እንደናፈቀ፣ እንደጠበቀ፣ ተስፋ እንዳደረገ፣ እና እንደ ታመነ፣ አሁን ደግሞ እሱ ለእግዚአብሔር ሕዝብ ጥሪ ያደርጋል፣ እንደርሱ ያደርጉ ዘንድ፡፡

የያህዌ ባሕርይ እንዴት እንደሆነ ተገንዘብ፡፡

1. እሱ ዘንድ ምሕረት አለ /ማለትም፣ ኪዳን፣ የታመነ ፍቅር፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት [ሄሰድ])
2. እሱ ዘንድ “ብዙ ማዳን” አለ /መዝ. 130፡7ሐ/
3. እሱ ዘንድ /ሌሎች ጋ ሳይሆን፣ የተእመቅ/ ማዳን አለ (ስም መዝ. 130:7 ላይ እና ግሥ መዝ. 130:8 ላይ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መዋጀት/መቤዠት/ በእርሱ ለሚታመኑት ሁሉ /ማለትም፣ የኪዳኑ ሕዝብ፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን እና ልዩ ርዕስ፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ/

የመጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት የተጠቃለለ እንደሆነ አስታውስ፡፡ እሱ ቤተሰባዊ ነው! ከዘመናዊው ምዕራባዊ ግለሰብ-ተኮር የተጋነነ አጽንዖት ተጠበቅ ደኅንነት የተጠቃለለ አትኩሮት አለው! እኛ የዳንነው ለማገልገል ነው፡፡ የግለሰብ መዳን ግብ የአማኞች ጤንነትና እድገት ነው!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝ. 130፡1-4ን ካነበብክ በኋላ ምን ዓይነት ስሜት ወደ ሐሳብህ/ልብህ መጣ?
2. “ጥልቅ” ምን ማለት እንደሆነ ታስባለህ?
3. እግዚአብሔር ኃጢአትን መዝግቦ ይጠብቃልን?
4. መዝ. 130፡5-6 የሚገልጸው ስለ እግዚአብሔርና ስለ ቃሉ ምን እንደሚሰማህ ነውን?

# መዝሙር 131
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ልጅነታዊ መታመን በጌታ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የመዓርግ የዳዊት መዝሙር<br><br>131:1-3 | ንጹሕ መታመን በጌታ | ለእግዚአብሔር ፍቃድና ምሪት በትሕትና መታዘዝ | የትሕትና መታመን ጸሎት | ልጅነታዊ መታመን |
| | 131:1<br>131:2<br>131:3 | 131:1-2<br>131:3 | 131:1-3 | 131:1-3 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 131፡1-3**

**[1]አቤቱ፥ ልቤ አይታበይብኝ፥ ዓይኖቼም ከፍ ከፍ አይበሉብኝ**
**ከትልልቆች ጋር፥**
**ከእኔም ይበልጥ ከሚከበሩ ጋር አልሄድሁም።**
**[2]ነፍሴን አሳረፍኋት፥**
**የእናቱንም ጡት እንዳስተውት ዝም አሰኘኋት**
**ነፍሴ የእናቱን ጡት እንዳስተውት በእኔ ውስጥ ናት።**
**[3]ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም**
**እስራኤል በእግዚአብሔር ይታመን።**

**131፡1 "ጌታ"** ይህ የኪዳን ስም ነው ለእስራኤል መለኮት /አምላክ/፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፡፡

▣ **"ልብ"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ሰውን /ግለሰብን/ የሚያመለክት፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ፡፡

▣ **"አይታበይ"** መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር የትሕትና አቋሙን ይገልጻል፣ በበርካታ ሐረጋት፣ መዝ. 131፡1-2፡፡
1. አይታበይ /"ከፍ ከፍ አይበል"/ – ቢዲቢ 146፣ ኬቢ 170፣ ቃል የተጠናቀቀ
2. ዓይኖቼም አይታበዩ ("ዓይኖቼ ከፍ ከፍ አይበሉ") – ቢዲቢ 926፣ ኬቢ 1202፣ ቃል የተጠናቀቀ
3. አልሄድኩም ("መራመድ፣" ቢዲቢ 229፣ ኬቢ 246፣ ፒል የተጠናቀቀ) ራሴ
   ሀ. በትልልቅ ነገሮች (ቢዲቢ 152)
   ለ. እጅግ አስቸጋሪ ከሆኑ ነገሮች (ቢዲቢ 810፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: ተአምራት) ለእኔ
4. ነፍሴን አሳረፍኳት – ቢዲቢ 1000፣ ኬቢ 1436፣ ፒል የተጠናቀቀ

5. ነፍሴን ዝም አሰኘኋት – ቢ.ዲ.ቢ. 198፣ ኬ.ቢ. 226፣ ፖል የተጠናቀቀ

ኩሩና ትዕቢተኛ ሰዎች የእግዚአብሔር ቁጣ ተቀባይ ናቸው (መዝ. 18:27፤101:5፤ሶፎ. 3:11) ምክንያቱም እሱ የዘፍጥረት 3ን ውድቀት ውጤት ስለሚገልጥ፡፡ ትሕትና የመንፈሳዊ መለወጥን ውጤትና የእግዚአብሔርን ራዕይ መቀበልን ያሳያል፡፡

ርግጠኛ ጥያቄ አለ የቁ. 3 ምናባዊነት ምን ማለት እንደሆነ፡፡

1. እንዲያው የትሕትና ፈሊጥ
2. እንዲያው የጥገኝነት ፈሊጥ
3. አንዱ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራ የማያጠይቅ
4. አንዱ የእግዚአብሔርን ኃይል የማይገምት
5. ሰው እሱም በነገሮች ቅንብር ውስጥ የራሱን/የራሷን ስፍራ የሚያውቅ /መዝ. 89፡10/

**131፡2** መዝሙረኛው የትሕትና ሁኔታ መግለጹን ቀጥሏል፣ የሕጻንን ምናባዊ ምስያ በመጠቀም፡፡

▣ **"ነፍስ"** ይህ ኔፊሽ ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 659)፣ መንገድ፣ እንደ "ልብ፣" የሰውን ሙሉ ቁመና የሚያመለክት፡፡ ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት ዘፍ. 35:18 ላይ፣ በድረ-ገጽ፡፡

**131:3** መዝሙረኛው የገዛ ራሱን ትሑት ልብ እና ሰላማዊ ተስፋ/መታመን/ትዕግሥት ይጠቀማል (ቢ.ዲ.ቢ. 403፣ ኬ.ቢ. 407፣ ፒል ተተኳሪ፣ መዝ. 130:5፣6፣7) ብሔረ-እስራኤልን ለማበረታታት፣ በተመሳሳይ ስፍራ፡፡

▣ **"ከዛሬ ጀምሮ እስከ ዘላለም"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ሦስት ቃላትን ይጠቀማል፣ በ" ህ" የሚጀምሩ (መዝ. 113:2፤115:18፤121:8፤125:2)፡፡

1. ቢ.ዲ.ቢ. 773 – ተውሳከ ግሥ ለወቅቱ ጊዜ (ማለትም፣ አንደኛ ሐረግ)
2. ቢ.ዲ.ቢ. 723 III – መስተጻምር
3. ቢ.ዲ.ቢ. 761 – ስም፣ ኦላም፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: ዘላለም (ኦላም)

# መዝሙር 132
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጆት** | **አየተመት** | **አእት** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ጸሎት ለጌታ ባርኮትበመቅደሱ ላይ | የእግዚአብሔር ዘላለማዊ መኖርያ በጽዮን | የአምልኮ ሥርዓት መታሰቢያ፣ እግዚአብሔር ጽዮንንና የዳዊትን ሥርወ-መንግሥት በመምረጡ | ምስጋና በመቅደስ | ስለ ታቦቱ መሸጋገር ክብረ-በዓል |
| <u>ኤምቲ መግቢያ</u><br>የመዓርግ መዝሙር | | | | |
| 132:1-5 | 132:1-5 | 132:1-5 | 132:1-5 | 132:1-5 |
| 132:6-9 | 132:6-9 | 132:6-7 | 132:6-7 | 132:6-7 |
| | | 132:8-10 | 132:8-9 | 132:8-10 |
| 132:10-12 | 132:10 | 132:11-12 | 132:10-12 | |
| | 132:11-12 | 132:13-18 | | 132:11-12 |
| 132:13-18 | 132:13-18 | | 132:13-18 | 132:13-14 |
| | | | | 132:15-16 |
| | | | | 132:17-18 |

### **የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር በግልጽ ስለ... ነው
1. እግዚአብሔር ለዳዊት ስለሰጠው ተስፋ 2 ሳሙ. 7:12-16፤2 ዜና. 6:16 (አጭር ማብራያ ተመልከት “የዳዊታዊ ኪዳን” ኒዶቲ፣ ቅጽ 4፣ ገጽ 507-508 ላይ)
2. እግዚአብሔር የሞሪያ ተራራን ስለ መምረጡ፣ እንደ መገኛው መኖርያው ስፍራ (ዘዳ. 12:5፣11፣14፣18፣21፣26፤14:23-25፤15:20፤ 16:2፣6፣11፣15፤17:8፣10፤18:6፤26:2፤31:11፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሞሪያ)

ለ. የእግዚአብሔር መገኘትና የእስራኤል የኪዳን ታዛዥነት
1. ለእርሷ ያላትን አትረፍርፎ ለመባረክ፣ መዝ. 132፡15
2. ረሀቧን ለማጥገብ፣ መዝ. 132፡15
3. ተአምራታዊ አምልኮ፣ መዝ. 132፡16
4. የእግዚአብሔር ንጉሥ ከፍ ከፍ ይላል፣ መዝ. 132፡17
5. የዳዊታዊው ንጉሥ ጠላቶች ጥፋት፣ መዝ. 132፡17

ሐ. ለመልካም አጭር ማብራሪያ፣ ለጽዮን ሥነ-መለኮት፣ ኒዶቴ ቅጽ 2፣ ገጽ 959 እና 512 ተመልከት፡፡

**መዝሙር ፡ 132፡1-5**

**[1]አቤቱ፥ ዳዊትን**
**ገርነቱንም ሁሉ አስብ**
**[2]ለእግዚአብሔር እንደ ማለ፥**
**ለያዕቆብም አምላክ እንደ ተሳለ።**
**[3]በእውነት ወደ ቤቴ ድንኳን አልገባም፥**
**ወደ ምንጣፌም አልጋ አልወጣም፥**
**[4]ለዓይኖቼም መኝታ**
**ለሽፋሽፍቶቼም እንቅልፍ፥**
**ለጕንጮቼም ዕረፍትን አልሰጥም፥**
**[5]ለእግዚአብሔር ስፍራ፥**
**ለያዕቆብ አምላክ ማደሪያ እስካገኝ ድረስ ብሎ።**

**132፡1 "አስብ"** ይህ ተተኳሪ ነው፣ እንደ ጸሎት ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ መዝሙር 25፡6-7 የሚያሳየው ይህ ጥቅም ላይ የዋለበትን መንገድ ነው፡፡

1. አምላክ፣ የማይለወጠውን የጸጋና የምሕረት ባሕርይህን አስብ፣ መዝ. 25፡6
2. አምላክ፣ ኃጢአታችንን ይቅር በል፣ መዝ. 25፡7

▣ **"ዳዊትን"** ዘወትር የእስራኤል ሕዝብ እና መሪዎቿ እግዚአብሔርን ይለምኑ ነበር ምሕረት እንዲያደርግላቸው፣

1. ለአባቶች ስለገባው ቃል /ማለትም፣ ለአብርሃም፣ ይስሐቅ፣ እና ያዕቆብ/
2. ለዳዊት ስለገባው ቃል /2 ሳሙኤል 7፤ 2 ዜና መዋዕል 6፡16/

▣ **"መከራውንም ሁሉ"** ይህ የዳዊትን መግለጫ የሚጠቅስ ይመስላል፣ 2 ሳሙ. 16፡12፣ ነገር ግን እሱ የዳዊትን የመነሻ ችግሮች የሚያመለክት ይመስላል፣ ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም ባመጣ ጊዜ /2 ሳሙኤል 6/፡፡ ጀፒኤስኦኤ እሱን የሚተረጉመው "የእርሱ እጅግ ራስን መካድ" በሚል ሲሆን፣ ይኸውም ከዘኍ. 30:13 እና 1 ዜና. 22:14 አጠቃቀም ጋር ይዛመዳል፡፡

LXX ኤምቲን ዳግም ያናብበዋል (ቢዲቢ 776 III፣ ኬቢ 853፣ ሥሯ ያልተጠናቀቀ አወቃቀር) "ከትሑትነቱ" ጋር (ስም፣ ቢዲቢ 776፣ መዝ. 45:4)፡፡

**132:2-5 "ለእግዚአብሔር እንደማለ"** ይህ መሐላ በታሪካዊ መጻሕፍት ላይ አልሰፈረም፡፡ ዳዊት በመሠረቱ

1. መሐላ አድርጓል፣ የማደሪያው ድንኳን ወደ ኢየሩሳሌም ስለ መምጣቱ
2. ወደ ራሱ ማደሪያ ስፍራ አልገባም /"ወደ ቤቴ ድንኳን"/ የማደሪያው ድንኳን /ማለትም፣ የያህዌ ማደሪያ ድንኳን/ በኢየሩሳሌም እስኪሆን
3. አይተኛም /ግነታዊ ዘይቤ/ ታቦቱ እስኪመጣ ድረስ
4. መዝ. 132፡5 የእርሱን ዓላማ ያስቀምጣል /ማለትም፣ የኪዳኑ ታቦት እና የማደሪያው ድንኳን በዋና ከተማው፣ ሐዋ. 7፡46/

ግልጽ የሆነው ቁ. 2 እና ቁ. 3 ግነታዊ መሆናቸው ነው፣ እናም ጥቅም ላይ የሚውሉት ለጽሑፋዊ ብልሃት ነው፣ የተጠናከረ ሐሳብን ለማሳየት!
**132:2 "የያዕቆብ አምላክ"** ይህ መጠሪያ (ቢዲቢ 7 አወቃቀር ቢዲቢ 784) ለእስራኤል አምላክ /መለኮት/ በቅድሚያ ጥቅም ላይ የዋለው ዘፍ. 49:24 ላይ ነው፣ ያዕቆብ ልጆቹን ሲባርክ፣ የወደፊቱን የእስራኤል ነገዶች፡፡ ደግሞም ኢሳ. 49:26 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል /ለዩኒቨርሳላዊው መዋጀት ተስፋ/ እና 60፡16፣ ይኸውም ከሌለኛው የያህዌ መጠሪያ ጋር የሚያያዝ፡፡

1. አዳኝ (ኢሳ. 19:2፤43:3፣11፤45:15፣21፤63:8)
2. የሚቤዥ (ኢሳ. 59:20፤63:16)

ኒዶቴ ቅጽ 1፣ ገጽ 232፣ አስደናቂ አስተያየት አለው፣ "ብርቱ" የሚለው ቅጽል ሁለት መልኮች አሉት፡፡

1. በዋነኛነት እሱ የሚጠቅሰው የበሬዎችን ወይም የዱር-በሬዎችን ጥንካሬ ለማመልከት ነው
2. የያህዌን ብርታት ለመግለጽ

**132፡5** ይህ የዳዊትን ፍላጎት፣ ቋሚ ቤተ-መቅደስ ለመሥራት ያለውን የሚጠቅስ አይደለም (1 ነገ. 8:17፤1 ዜና. 22:7) ነገር ግን ታቦቱን ከተንቀሳቃሽ ድንኳኑ ጋር ለማምጣት እንጂ /ማለትም፣ የማደርያ ድንኳን የዘጸአት ጊዜ/ ወደ ዋና ከተማው፣ ኢየሩሳሌም /2 ሳሙኤል 6/፡፡

▣ **"ማደርያ ስፍራ"** ይህ የብዙ ቁጥር ነው፣ ኤምቲ ላይ፣ እናም ጠቃሚነትን መግለጫ ሰዋሰዋዊ መንገድ ሊሆን ይችላል፣ እንደ አእት "ያማረ ማደሪያ ስፍራ፡፡"

በሌሎች ዐውደ-ጽሑፎች ላይ ይህ ቃል በብዙ ቁጥር የሚገልጸው ሁሉንም ሕንፃዎች ነው፣ በመቅደስ ዙሪያ ያሉትን (መዝ. 43:3፤46:4፤ 84:1)፡፡

**መዝሙር ፡ 132፡6-9**

**[6]እነሆ፥ በኤፍራታ ሰማነው፥**
**በዱር ውስጥም አገኘነው።**
**[7]ወደ ማደሪያዎቹ እንገባለን**

**እግሮቹ በሚቆሙበት ስፍራ እንሰግዳለን።**
**[8]አቤቱ፥ ወደ ዕረፍትህ ተነሥ፥**
**አንተና የመቅደስህ ታቦት።**
**[9]ካህናቶችህ ጽድቅን ይልበሱ፥**
**ቅዱሳንህም ደስ ይበላቸው።**

**132፡6 "ኤፍራታ"** ይህ በይሁዳ ያለ ስፍራ ነው፣ እሱም የዳዊትን ቤተሰብ ዝርያ የሚጠቅስ /ሩት 4፡11/፡፡ ሆኖም፣ ቤተልሔም የታቦቱ ስፍራ አይደለችም፡፡ እነሱ ስለ ንጉሡ መሐላ ብቻ ሰምተዋል (መዝ. 132:2) ታቦቱን ወደ ኢየሩሳሌም እንደሚያመጣ፡፡

▣ **"ጃር"** ይህ የኪሪዝ-ጃሪም ጠቃሽ ነው (1 ሳሙ. 7:1፤1 ዜና. 13:1-8)፣ ታቦቱ በግል ቤት ለሃያ ዓመት የነበረበት፣ ዳዊት ወደ ኢየሩሳሌም ከማምጣቱ በፊት፡፡ "ጃር" የ"ጃሪም" ነጠላ ቁጥር መልክ ነው፡፡

▣ **"እሱ"** ይህ የአንስታይ /ሴቴ ጾታ/ ድኅረ-ቅጥያ ነው፣ "ታቦቱ" ተባዕታይ ሲሆን፣ ስለዚህ እሱ የዳዊትን መሐላ የሚጠቅስ ሊሆን ይችላል (ኒዶቴ ቅጽ 3፣ ገጽ 736፤ኤቢ፣ ገጽ 244) መዝ. 132:2 ላይ ተጠቅሷል፡፡

አእመቅ (ገጽ 1000) የሚጠቅሰው ሐቅ ቢያንስ በሁለት ገጠመኞች ላይ "ታቦት" በአንስታይ ተጠቅሷል (ማለትም፣ 1 ሳሙ. 4:17፤2 ዜና. 8:11)፡፡ ይህ መዝሙር በርካታ የድሮ ቃላትና መልኮች በመያዙ ምክንያት ይህ የጾታ ችግርን ይፈታል፡፡

**132፡7** ሁለቱም ቁጥሮች ተጓዳኝ የብዙ ቁጥር ሲሆኑ የሚያመለክቱትም ወደ ያህዌ ቤተ-መቅደስ የሚደረግን ምነና /ጉዞ/ ነው፡፡

▣ **"የእግሮች መቆሚያ"** ሁለቱም ዳዊት (1 ዜና. 28:2) እና ሰሎሞን (1 ነገ. 8:27) እውቅና ሰጥተዋል፣ መቅደሱ እውነተኛው የፍጥረት አምላክ ማደሪያ ስፍራ ላለመሆኑ፡፡ ዳዊት መጥራት ጀመረ፣ ከኪሩቤል ክንፎች መካከል ከምሕረት መኖርያው /የታቦት መክደኛ/ በላይ ያለውን ስፍራ ሰማይና ምድር፣ የማይታየውና የሚታየው፣ ዘላለማዊውና ጊዜያዊው የሚጋጠሙበት /ዘጸ. 25፡22/! እሱንም የያህዌ የእግር መቀመጫ ብሎ ጠርቶታል" (ኢሳ. 66፡1፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የኪዳን ታቦት)፤ ደግሞም መዝ. 99፡5 ላይ ማስታወሻ።

ይህ የመለኮት ምናባዊ ምስያ እግሮች እንዳለው የሚገልጸው የሰውን ቃል ውስንነት የሚያሳይ ነው፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አምላክ እንደ ሰው ሲገለጽ /አንትሮፖሞርፊዝም/፡፡

**132፡8 "ተነሥ"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 877፣ ኬቢ 1086፣ ቃል ተተኳሪ) ዘኍ. 10:35 እና 2 ዜና. 6:41 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ያህዌ ከዙፋን መነሣቱን፣ በሕዝቡ ፊት ሆኑ ስለ እነርሱ ሊዋጋ መሆኑን የሚገልጽ ነው (መዝ. 3:7፤7:6፤9:19፤10:12፤44:26፤74:22፤82:8)፡፡

ይህ ቁጥርና መዝ. 132:9 ጠቃሽነታቸው የሰሎሞንን አዲሱን መቅደስ ምርቃት ይመስላል፣ 2 ዜና. 6፡41፡፡

▣ **"የእግሮች መቆሚያ"** ያህዌ በሰው ቋንቋ ተገልጿል፣ ሌላ ዐውደ-ቃላት በመጽሐፍ ቅዱስ ጸሐፍት ዘንድ ሊገኝ ባለ መቻሉ ምክንያት /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰዎች ሲገለጽ /አንትሮፖሞርፊዝም/፡፡ የኪዳኑ ታቦት እና፣ ከዚያም ያህዌ ራሱ፣ ይሻል/ይፈልጋል ሥጋዊ ስፍራ ለእሱ/ለታቦቱ//ለእርሱ/ለያህዌ/ እዛው ለመሆን/ለማረፍ (1 ዜና. 6:31፤28:2፤2 ዜና. 6:41፤መዝ. 132:8፤14፤ኢሳ. 11:10፤66:1)፡፡ አንትሮፖሚርፊክ ምናባዊ ምስያ ለእግዚአብሔር ወሰን አያስቀምጥም ነገር ግን ለሰዎች ችሎታ ውስንነት እንጂ፣ የጊዜና የስፍራን አምላክ ከማስቀመጥ አኳያ /ማለትም፣ ሥጋዊ ፍጥረት/፡፡

አዲስ መጽሐፍ በጆን ዋልተን፣ *የዘፍጥረት አንድ የጠፋው ዓለም፡* የጥቅምን /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/ ሥነ-ፈለክ ይጠቀማል፣ ዘፍጥረት 1 የሚያሳየው የያህዌን ሐሳብ ነው ሥነ-ፈለካዊ መቅደስ በመገንባት /ማለትም፣ ምድር/ እንደ ዕረፍት ስፍራ /ዘፍ. 2፡1-3/፡፡

ዕብራውያን 3:7 እስከ 4:13 (መዝ. 95:7-11) "ዕረፍት" የሚለው ቃል ቅይይር /ጨዋታ/ አለው፣ ሦስት የተለያ ነገሮችን በመጥቀስ፡፡

1. ሰባተኛ የፍጥረት ቀን ከዘፍ. 2:2 ዕብ. 4:3፣4፣10 ላይ
2. የተስፋይቱ ምድር ከዘኁልቁ 13-14 ዕብ. 3:11፣18፤4:8 ላይ
3. የፍጻሜ ዘመን ሰማይ

"ዕረፍት" ሁለቱንም ነው፣ የሰላም ስሜት እና የሚመኙት የኅብረት ስፍራ (መዝ. 62:1፤ኢሳ. 63:14፤ኤር. 31:2)፡፡

**132:9** ይህ ቁጥር ሁለት ያልተጠናቁ አሉት፣ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ፡፡

1. ይልበሱ – ቢዲቢ 527፣ ኬቢ 519፣ ቃል
2. በደስታ ይዘምሩ – ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247፣ ፒል

ሁለት ቡድኖች ለመጠቀሳቸው ርግጠኝነት የለም /ማለትም፣ ካህናት እና ምዕመናን/ ወይም ጽሑፋዊ ትይዩ፡፡

ኢዮብ 20፡14 ላይ ኢዮብ ራሱን ይገልጻል፣ ጽድቅን እንደለበሰ፡፡ እሱም በርግጠኝነት ምን ማለት እንደሆነ አይገልጽም፣ ከእነዚህ ካህናት ጋር በተያያዘ፡፡ እነርሱ የያህዌን ባሕርይና ራዕዩን ያንጸባርቃሉ፣ በመሪነታቸው፣ በሕይወታቸው፣ በሥራቸው፣ እና በተግባራቸው፡፡

ይህ ቁጥር የሚያንጸባርቀው በዓላዊና በፍርሃት የተሞላውን ጉዞ ነው፣ ታቦቱን ልዩ ልብስ የተጎናጸፉ ካህናት ተሸክመውት፣ ሌዋውያን እየዘመሩ፡፡

### መዝሙር ፡ 132፡10-12

**[10]ስለ ዳዊት ስለ ባሪያህ**
**የቀባኸውን ሰው ፊት አትመልስ።**
**[11]እግዚአብሔር ለዳዊት**
**በእውነት ማለ አይጸጸትምም፥**
**እንዲህ ብሎ። ከሆድህ ፍሬ በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ።**

[12]**ልጆችህ ኪዳኔን፥**
**ይህንም የማስተምራቸውን ምስክሬን ቢጠብቁ፥**
**ልጆቻቸው ደግሞ በዙፋንህ ላይ ለዘላለም ይቀመጣሉ።**

**132፡10-12** ይህ አንጓ በርግጥ 2 ሳሙኤል 7ን ይጠቅሳል፡፡ የመዝ. 132፡12ን ሁኔታዊ ይዘትን ተገንዘብ፣ ከእያንዳንዱ ግለሰብ ዝርያ ጋር የተያያዘውን፣ ነገር ግን ትልቁ የእግዚአብሔር ዓላማ 2 ሳሙ. 7፡14-16 ላይ ተገልጿል፡፡

የድምጽ መቀያር /ጨዋታ/ በብዙዎቹ ግሦች ላይ መደረጉን ተገንዘብ መዝ. 132:10-12 **፪**፡፡

1. ፊት አትመልስ – ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ *ሂፊልተጽዕኗዊ*
2. እንደ ማለ – ቢዲቢ 989፣ ኬቢ 1396፣ *ኒፋል* የተጠናቀቀ
3. አይመለስም – ተመሳሳይ ሥር ከቁ. 1 ጋር፣ ግን *ቃል* ያልተጠናቀቀ
4. በዙፋንህ ላይ አስቀምጣለሁ – ቢዲቢ 1011፣ ኬቢ 1483፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
5. ልጆችህ ኪዳኔን ቢጠብቁ – ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ (ሁኔታዊውን ገጽታ ተገንዘብ፣ 1 ነገ. 9:4-9፤መዝ. 89:30-45)

**132:10 "የቀባኸውን"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 603) "መሲሕ" የሚለው መጠሪያ የመጣበት ነው፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መሲሕ፡፡

**132፡12 "ኪዳን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን፡፡

▣ **"ምስክር"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ፡፡

▣ **"ዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም /ኦላም/፡፡

**132:11 "እግዚአብሔር ለዳዊት እንደማለ"** ዳዊት እንደማለ መዝ. 132፡2 ላይ፣ አሁን ደግሞ ያህዌ በገዛ ራሱ መሐላ ምላሽ ሰጥቷል፡፡ ይህም መሐላ የዳዊት ኪዳን በመባል ይታወቃል (2 ሳሙኤል 7፤መዝ. 89:3፣35)፡፡

## *መዝሙር* ፡ 132፡13-18

[13]**እግዚአብሔር ጽዮንን መርጦአታልና፥**
**ማደሪያውም ትሆነው ዘንድ ወድዶአታልና፥ እንዲህ ብሎ።**
[14]**ይህች ለዘላለም ማረፊያዬ ናት**
**መርጫታለሁና በዚህች አድራለሁ።**
[15]**አሮጊቶችዋን እጅግ እባርካለሁ፥**
**ድሆችዋንም እንጀራ አጠግባለሁ።**
[16]**ካህናቶችዋንም ደኅንነትን አለብሳቸዋለሁ፥**
**ቅዱሳኖችዋም እጅግ ደስ ይላቸዋል።**
[17]**በዚያ ለዳዊት ቀንድን አበቅላለሁ፥**
**ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ።**
[18]**ጠላቶችንም እፍረትን አለብሳቸዋለሁ**
**በእርሱ ግን ቅድስናዬ ያብባል።**

**132፡13-18** ይህ አንጓ እግዚአብሔር ያደረገውን ነገር ይገልጻል (መዝ. 132:13-14) የሚያደርገውንም (መዝ. 132:15-18)፡፡

1. ጽዮንን መርጧታል (ልዩ ርዕስ ተመልከት: ጽዮን)፣ መዝ. 132:13-14
2. አትረፍርፎ ይባርካል (ግነታዊ ያልተወሰነ የተጠናቀቀ እና ያልተጠናቀቀ ግሥ ከተመሳሳይ ሥር፣ ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159)፣ መዝ. 132:15*ሀ*
3. ምግብ ይሰጣል፣ መዝ. 132:15*ለ*
4. የመቅደሱ ካህናት ቅዱሳን ሰዎች ይሆናሉ፣ መዝ. 132:16 (1 ዜና. 6:41)
5. የመቅደሱ ምዕመናን (መዝ. 4:3 ወይም ሌዋውያን) በደስታ ይዘምራሉ (ግነታዊ ያልተወሰነ የተጠናቀቀ እና ያልተጠናቀቀ ግሥ፣ ከተመሳሳይ ሥር፣ ቢዲቢ 943፣ ኬቢ 1247)፣ መዝ. 132:16 (1 ዜና. 6:41)
6. የዳዊትን ሥርወ-መንግሥት በኢየሩሳሌም ያጸናል፣ መዝ. 132፡17
7. የእስራኤልን ጠላቶች ያሸንፋል፣ መዝ. 132፡18

**132፡16** በዚህ አንጓ ትይዩዎች የተነሣ፣ "ካህናት" የሚለው /ወይም ሌዋውያን/ በሁለቱም ስንኞች ላይ ተመልከተዋል፣ በዚህ ቁጥር፡፡

**132፡17 "የዳዊት ቀንድ"** ቀንድ የዕብራውያን ፈሊጥ ነው የኃይልና ቅድመ-ብርታት /ሉቃስ 1፡69/፡፡

▣ **"መብቀል"** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 855፣ ኬቢ 1033፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ) ሊዛመድ የሚችለው ከተለየው የዳዊታዊ ንጉሥ፣ "ቅርንጫፍ" ተብሎ ከሚጠራው ጋር ነው፡፡ ተመልከት፡

1. ልዩ ርዕስ፡ የናዝሬቱ ኢየሱስ

2. ሙሉ ማስታወሻ ኢሳ. 11፡1 ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር
3. ኒዶቲ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 75

ለ"አክሊል" ሥሩ ገ፤ነ ነው፣ እሱም የሚገልጸው

1. አክሊል (ስም፣ ቢ.ዲ.ቢ. 634)
2. መቀደስ (ግሥ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 634)
3. ቅርንጫፍ (የመሲሕ መጠሪያ)

▣ ***"ለቀባሁትም ሰው መብራትን አዘጋጃለሁ።"*** ይህ የተወሰነ አጠቃቀም ነው፣ ለብርሃን ምናባዊነት፣ እሱም ራዕይን የሚጠቅስ ያይደለ (ማለትም፣ መዝ. 18:28፤119:105፤ምሳ. 6:23) ነገር ግን ለዳዊት ዝርያ፣ በእስራኤል ዙፋን ላይ ለሚቀመጥ (1 ነገ. 11:36፤15:4፤2 ነገ. 8:19፤2 ዜና. 21:7)፡፡ 2 ሳሙ. 21:17 ላይ እሱ የሚጠቅሰው ዳዊትን ራሱን ነው፡፡

# መዝሙር 133
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የወንድማማች ኅብረት ክብር<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት የመዓርግ መዝሙር<br>133፡1-3 | የእግዚአብሔር ሕዝብ የተባረከ ኅብረት<br>133፡1<br>133፡2-3 | በቤተሰብ ያለ የኅብር ደስታ<br>133፡1-3 | ምስጋና በሰላም ስለ መኖር<br>133፡1-3 | የወንድማማች ፍቅር<br>133፡1<br>133፡2-3 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ አጭር መዝሙር ለመተርጎም አስቸጋሪ ነው፣ በምናባዊ ምስያው ምክንያት፣ እሱም አንድ ላይ ደኅና አድርጎ ያልተገጣጠመ
1. ወንድሞች — አሮን
2. ሔርሞን — ጽዮን

ለ. የዚህ መዝሙር ሥነ-መለኮታዊ ዓላማና ታሪካዊ ጊዜም አይታወቅም፡፡ አንዳንዶች እንደሚዛመድ የሚመለከቱት
1. የዳዊት ጊዜ /በኤምቲ ርዕስ ምክንያት/ እስራኤልና ይሁዳ አንድ ላይ እንደነበሩ /2 ሳሙኤል 5፣ ማለትም፣ የተባበረው መንግሥት/
2. ድኅረ-ግዞት ጊዜ፣ እስራኤል /ሔርሞን ተራራ/ እና ይሁዳ /ጽዮን ተራራ/ ዳግም የተዋሀዱበት ጊዜ /ማለትም፣ የሲረስ አዋጅ፣ 538 ቅ.ል.ክ./
3. የሁሉም ደረጃ አይሁድ ኅብረተሰብ የጋራ ኅብረት ማድረጉን የሚያስረግጥ መዝሙር /ማለትም፣ የተለየ የቅባት ዘይት በአሮን ፂም እስከ ልብሱ "ሁሉ" ላይ መውረዱ/
4. እግዚአብሔር ሕዝቡ ሁሉ እንዲለማመደው የሚሻውን ማስረገጫ መንገድ
   ሀ. የተትረፈረፈ ሕይወት አሁን
   ለ. የዘላለም ሕይወት አንድ ቀን
5. ሁሉም ባርኮቶች "የሚወርዱት" (3 ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል – ቢዲቢ 432፣ ኬቢ 434፣ *ቃል* አንቀጽ) ከእግዚአብሔር ነው
   ሀ. የኪዳኑ ሕዝብ /ወንድሞች/
   ለ. ኅብረት /የአሮን ልብስ/
   ሐ. ባርኮቶች /ማለትም፣ ጠል
   መ. የዘላለም ሕይወት /መዝ. 133፡3ሐ/

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 133፡1-3**
**[1]ወንድሞች በኅብረት ቢቀመጡ፥**

**እነሆ፥ መልካም ነው፥ እነሆም፥ ያማረ ነው።**
[2]**ከራስ እስከ ጢም**
**እንደሚፈስስ፥**
**እስከ አሮን ጢም፥**
**በልብሱ መደረቢያ እንደሚወርድ ሽቱ ነው።**
[3]**በጽዮን ተራሮች እንደሚወርድ**
**እንደ አርሞንዔም ጠል ነው**
**በዚያ እግዚአብሔር በረከቱን ሕይወትንም እስከ ዘላለም አዝዞአልና።**

**133:1 "እነሆ፥ መልካም ነው፥ እነሆም፥ ያማረ ነው።"** እነዚህ ቅጽሎች (ቢ.ዲ.ቢ. 373 II እና ቢ.ዲ.ቢ. 653 I) የሚገልጹት በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠሩትን ሰዎች አንድ ማኅበረሰብ መሆንን እንዲለማመዱ መታሰቡን ነው፡፡

▣ **"ወንድሞች"** ይህ በትክክል ለማን እንደሆነ ርግጠኝነት የለም፣ ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ለ፡፡

▣ **"ማደር"** ይህ ስም (ቢ.ዲ.ቢ. 443 I) ከግሡ ጋር ይዛመዳል (ዲ.ቢ. 442) ፍችውም "መቀመጥ" ነው /ማለትም፣ የአንድነት ግብዣ/፣ "መቅረት" /ማለትም፣ አብሮ መኖር/፣ ወይም "ማደር" /ማለትም፣ መኖርያ ስፍራ/፡፡ እዚህጋ በጥሬው ወይም በዘይቤአዊነት ሊሆን ይችላል/፡፡

**133:2**
**አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣**

| | |
|---|---|
| **አየተመቅ** | **"የከበረ ዘይት"** |
| **አእቅ** | **"የከበረ የቅብዓት ዘይት"** |
| **አኢመቅ፣ ጀፒኤስአኤ** | **"ያማረ ዘይት"** |
| **የተእመቅ፣ LXX** | **"የሽቱ ዘይት"** |

ቅጽሉ (ቢ.ዲ.ቢ. 373 II) መዝ. 133:1 ላይ ጥቅም ላይ ከዋለው ጋር ተመሳሳይ ነው፡፡ (ማለትም፣"መልካም")፡፡

"ዘይት" የሚለው ስም (ቢ.ዲ.ቢ. 1032) ፍችው የሚሆነው "ስብ" ወይም "የወይራ ዘይት" ነው፡፡ የአሮን ዘይት በመጠቀሱ ምክንያት፣ መዝ. 133:2ሐ-መ፣ ይህ የሚያመለክተው የእርሱን ልዩ የተመረቀ የአገልግሎት ተልዕኮ ነው፡፡ (ዘጸ. 29:7፤30:25፤30፤ሌዋ. 8:12፤21:10)፡፡

የእስራኤል ሊቀ-ካህን ሁለቱንም ሃይማኖታዊ መሪ እና የፍጻሜ ዘመን መሲሐዊ መሪ ነው /ዘካርያስ 3-4/፡፡ ስለዚህ እሱ ተምሳሊት የሚሆነው

1. የእግዚአብሔር ብኪ ሕዝብ ኅብረት
2. በእግዚአብሔር መልክ የተፈጠሩት ሰዎች ሁሉ ኅብረት

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀቅ** | **"እስከ መደረቢያው ጫፍ"** |
| **አየተመቅ፣ አእቅ፣** | |
| **አኢመቅ፣ ጀፒኤስአኤ** | **"በልብሱ መደረቢያ ላይ"** |
| **የተእመቅ** | **"በልብሱ መደረቢያ ላይ"** |
| **LXX** | **"እስከ ልብሱ ጫፍ ድረስ"** |

የስሙ ፍች (ቢ.ዲ.ቢ. 804) የትርጓሜ ጉዳይ ነው፡፡ ጥሬ ትርጉሙ "አፍ" ነው፡፡ እሱም እዚህ የሚያመለክተው ዘጸአት 28ን ነው፣ የሊቀ-ካህኑ መደረቢያ/ኤፉድ ልዩ ቋድ /ማሰሪያ/፣ እሱም ሊቀደድ የማይችል /ማለትም፣ የዕብራይስጥ የኅዘን ተምሳሊት/፡፡ የትርጓሜ ጥያቄ የሚሆነው "ምን ያህል ዘይት ጥቅም ላይ ይውላል?" የሚል ነው፡፡ እሱም የኅብረት ተምሳሊት ነው /ማለትም፣ በካህናዊ ልዩ ልብስ ላይ ከላይ እስከ ታች የሚወርድ/? ይህ መዝሙር ስለ እስራኤል/አይሁድ ወገኖች ኅብረት ነውን ወይስ ስለ ሁሉም የሰው ልጅ (ማለትም፣ መዝ. 133:3ሐ)?

ለማስታወሻ ያህል፣ ሁለት ታሳቢ ሥሮች አሉ፣ ይህ "አንገትጌ" የሚለው ቃል የተወሰደበት፡፡

1. ልብስ፣ ጨርቅ – מד (ቢ.ዲ.ቢ. 551)
2. መለካት – מדד (ቢ.ዲ.ቢ. 551)

**133:3** አርሞንዔም ተራራ እንዴት ከጽዮን ተራራ ጋር ይዛመዳል?

1. የተስፋይቱ ምድር ኅብረት
2. የእስራኤል ነገዶች ኅብረት
3. የሕዝቦች ሁሉ ኅብረት፣ በፍጻሜ ዘመን መቼት /ማለትም፣ መዝ. 133፡3 እዚህጋ "ሕይወት" አሁን ማለት ነው፣ ወይስ "ሕይወት" በፍጻሜ ዘመን መቼት?/

▣ **"የአርሞንዔም ጠል"** እዚህ ከፍታ ተራራ ላይ ጠሉ ከሰሜን እስራኤል በቀላሉ ይታያል፣ እጅግም ግዙፍ ነበር፣ እናም ለመተረፍረፍ ፈሊጥ ሆኗል፡፡ የጽዮን ተራራ፣ በያህዌ ባርኮቶች በኅብረታቸው፣ ተመሳሳይ ርጥበት አላቸው፡፡

▣ **"ዘላለም"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል /ቢ.ዲ.ቢ. 761፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም [ዑላም]) መተርጎም የሚኖርበት በተወሰነ ዐውደ-ጽሑፍ ነው፡፡ ሥነ-መለኮታዊ ጉዳዩ የብኪን ታሳቢ የከሕይወት በኋላ ስሜትን ያካትታል፡፡ ምንም ጥርጥር አይኖርም፣ ቀጣይነት ባለው ራዕይ /ማለትም፣ አኪ/

መጽሐፍ ቅዱስ በጥቅሉ ይሄንን እውነት በግልጽ ያስረግጣል፣ ግን ብኪ ያደርጋልን? እኔም ይመስለኛል (ማለትም፣ ኢዮብ 14:14-15፤19:25-27) ግን ሁልጊዜ አይደለም (ማለትም፣ መዝ. 23:5፤27:4-6)፡፡ ሆኖም፣ ብኪ ላይ እንኳ ቢሆን፣ ለተስፋ ፍንጭ አለ፡፡

1. ሔኖክ (ዘፍ. 5:24) እና ኤልያስ (2 ነገሥት 2) ወደ ሰማይ ተወስደዋል
2. መዝሙር ላይ፣ መዝ. 1:3፤49:15፤73:24
3. ኢሳይያስ ላይ፣ ኢሳ. 26:19
4. ዳንኤል ላይ፣ ዳን. 12:1-4

# መዝሙር 134
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የሌሊት ትጋት ሰላምታ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የመዓርግ መዝሙር<br>134፡1-3 | እግዚአብሔርን ማመስገን በሌሊት በቤቱ<br>134፡1-2<br>134፡3 | የባርኮት አምልኮ ሥርዓት<br>134፡1-2<br>134፡3 | እግዚአብሔርን ለማስገን ጥሪ<br>134፡1-2<br>134፡3 | ለሌሊት የአምልኮ ሥርዓት<br>134፡1-2<br>134፡3 |

**የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 134፡1-3**
**[1]እነሆ፥ እግዚአብሔርን ባርኩ፥**
**በአምላካችን ቤት አደባባዩች የምትቆሙ እናንተ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሁላችሁ።**
**[2]በሌሊት በቤተ መቅደስ ውስጥ እጆቻችሁን አንሡ፥**
**እግዚአብሔርንም ባርኩ።**
**[3]ሰማይንና ምድርን የሠራ**
**እግዚአብሔር ከጽዮን ይባርክህ።**

**134፡1 "ባርኩ"** ይህ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 138፣ ኬቢ. 159) ሦስት ጊዜ ይከሰታል፣ በዚህ አጭር መዝሙር ላይ፡፡
1-2. ፒይል ተተኳሪ – መዝ. 134፡1፣2
3. ፒይል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ – መዝ. 134፡3
ተመሳሳይ /ቢ.ዲ.ቢ. 80/ ዘወትር መዝሙር ላይ ይከሰታል፡፡ ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 1፡1 ላይ፡፡ ለዚህ ቃል /ቢ.ዲ.ቢ. 139/ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ባርኮት /ብኪ/፡፡ መዝ. 1፡1 ላይ የሚባረከው ታማኝ ተከታይ ነው፣ እዚህ*ጋ* የእስራኤል አምላክ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት/፡፡

▣ **"የእግዚአብሔር ባርያዎች ሁሉ"** ይህ የሚገልጸው ንቁ የሆነውን ፍጡር ነው /ማለትም፣ መላእክት፣ ሰዎች፣ በሌላ ደረጃ ላይ ያሉ መንፈሳዊ ሕላዌዎች፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መላእክት በጳውሎስ ጽሑፎች/፡፡ የዚህ ጽንሰ-ሐሳብ የተሻለ ትይዩ /1/ መዝ. 103፡19-22 ነው፣ እዚያም ተመሳሳይ ግሥ ለመላእክት ዓለም ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ፤ /2/ መዝ. 135፡1-4፣ እዚያም ሦስት "ምስጋናዎች" (ቢ.ዲ.ቢ. 237፣ ኬቢ. 248፣ ፒል ተተኳሪ) ለካህናትና ሌዋውያን ጥቅም ላይ የዋሉ፡፡
አምስት የተለያዩ ዓይነቶች የመቅደስ አገልጋዮች አሉ፡፡
1. ካህናት
2. ሌዋውያን
3. መዘምራን
4. በረኞች

5. ዝቅተኛ አገልጋዮች /ኒዶቴ ተመልከት፣ ቅጽ 3 ገጽ 203-204/

▣ **"በሌሊት በአምላካችን ቤት አደባባዬች የምታገለግሉ"** ይህ በድጋሚ ተገልጿል፣ መዝ. 135፡1-4 ላይ፡፡ የሚያመለክተውም፣ የሌዊን ቤተሰብ ነው፣ ከአሮን እሱም በኢየሩሳሌም ቤተ-መቅደስ የሚያገለግለው /"መቆም" ቢ.ዲ.ቢ. 763፣ ኬ.ቢ. 840፣ በአጽንዖት የሚያመለክተው የቤተ-መቅደስ ካህናትን ወይም ሌዋውያንን ነው/፡፡ መስተጻምራዊው ሐረግ፣ "በሌሊት" /ቢ.ዲ.ቢ. 538/ ፍችው "ቀኑን ሁሉ፣" ነው፣ በሌሊት የሚተጉትን ብቻ ሳይሆን /1 ዜና. 9፡33/፡፡

ትይዩ ሐረግ አለ መዝ. 135፡2 ላይ እሱም ተጨማሪ ገላጭ ሐረግ የሚያክል /ማለትም፣ LXX፣ አኢ.መቅ/፡፡

**134:2 "በቤተ መቅደስ ውስጥ እጆቻችሁን አንሡ፥"** *ግሥ* (ቢ.ዲ.ቢ. 669፣ ኬ.ቢ. 724፣ *ቃል ተተኳሪ*) የሚገልጸው የካህናትን ተግባር ነው፡፡ ዘኍ. 6:24-26፤ሌዋ. 9:2፣ ላይ እነርሱ ይባርካሉ (ቢ.ዲ.ቢ. 138፣ ኬ.ቢ. 159) ሕዝቡን፣ እጆቻቸውን በማንሣት፣ እዚህ ግን እነርሱ ያህዌን "ይባርካሉ" በመቅደሱ የሚኖረውን፣ በኪሩቤል ክንፎች መካከል፣ በ "ምሕረት መንበሩ"፣ በቅድስተ ቅዱሳን፡፡

"እጆችን ማንሣት" የሚለው ሐረግ በርካታ የተለዩ ነገሮችን ሊጠቅስ ይችላል፡፡

1. መሐላ መፈጸም – ዘፍ. 14:22፤ዘጸ. 6:8፤ዘኍ. 14:30፤መዝ. 106:26፤ሕዝ. 20:5 (በአንድምታ ዕዝራ 10:5 ላይ)
2. የዓመጻ ድርጊት – 2 ሳሙ. 20:21
3. ለመባረክ – ሌዋ. 9:22፤መዝ. 134:2፤ሉቃስ 24:50፤1 ጢሞ. 2:8
4. የያህዌ ድርጊቶች ምልክት – መዝ. 10:12፤ሚክ. 5:9
5. አካላዊ ምልክቱ ጸሎትን የሚጠቅስ አጠቃላይ መንገድ ነው – ዘጸ. 9:29፣33፤1 ነገ. 8:22፣38-39፤ዕዝራ 9:5፤መዝ. 28:2፤63:4፤141:2፤1 ጢሞ. 2:8

የሮዘርሃም አጽንዖታዊ መጽሐፍ ቅዱስ "መቅደስ"ን የሚተረጉመው ካህናቱን ራሳቸውን በሚያመለክት መንገድ ነው (ማለትም፣ እጆቻችሁን በቅድስና አንሡ፣ ሌዋ. 21:6፤2 ዜና. 23:6፤ዕዝራ 8:28)፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቅዱስ፡፡

**134:3ሀ** ይህ የቅኔ ስንኝ የሚያመለክተው የሁለትዮሽ ግንኙነትን ነው፣ ያህዌን በመባረክ /ማለትም፣ ማምለክ/ መካካል እና በእርሱ ባርኮት (ቢ.ዲ.ቢ. 138፣ ኬ.ቢ. 159፣ ፒኤል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ) የኪዳኑን ሕዝብ (መዝ. 128:5)፡፡

▣ **"ጽዮን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽዮን፡፡

**134:3ለ** ያህዌ በባሕርዩ ፈጣሪ ነው (መዝ. 115:15፤121:2፤124:8፤134:3፤136:5፤146:6)፡፡ ይህ የማጠቃለያ ሐረግ ለሥነ-መለኮታዊው ግፊት ፍንጭ ሊሰጥ ይችላል፣ ለመዝ. 134:1፣ ማለትም "አገልጋዮቹ" ሁለቱም ሕይወት የሌላቸውና ሕይወት ያላቸው ፍጡራንን እንደሚያካትት፡፡

# መዝሙር 135
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| **አአመመቅ** | **አኪጀት** | **አየተመት** | **አእት** | **አኢመቅ** |
|---|---|---|---|---|
| ጌታን ስለ ድንቅ ሥራው ማመስገን፡፡ የጣዖታት ከንቱነት <u>ኤምቲ መግቢያ የለውም</u> | እግዚአብሔርን ማመስገን ስለ መፍጠሩና መዋጀቱ | ውዳሴ ምስጋና ለጌታ ስለ ብርቱ ሥራው | የውዳሴ ምስጋና | የውዳሴ ምስጋና |
| 135:1-4 | 135:1ሀ | 135:1-4 | 135:1-4 | 135:1ሀ |
| | 135:1ለ-4 | | | 135:1ለ-2 |
| | | | | 135:3-4 |
| 135:5-7 | 135:5-7 | 135:5-7 | 135:5-7 | 135:5-6 |
| | | | | 135:7 |
| 135:8-18 | 135:8-12 | 135:8-12 | 135:8-12 | 135:8-9 |
| | | | | 135:10-12 |
| | 135:13-14 | 135:13-14 | 135:13-14 | 135:13-14 |
| | 135:15-18 | 135:15-18 | 135:15-18 | 135:15-16 |
| | | | | 135:17-18 |
| 135:19-21 | 135:19-21ለ | 135:19-21 | 135:19-21ለ | 135:19-20 |
| | | | | 135:21ሀ-ለ |
| | 135:21ሐ | | 135:21ሐ | |

### **የንባብ ምድብ ሦስት** (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. *የመጀመሪያው አንቀጽ*
2. *ሁለተኛው አንቀጽ*
3. *ወዘተርፈ*

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የሚጀምረውና የሚጨርሰው በ
1. ምስጋና – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ፒል ተተኳሪ፣ መዝ. 135:1 (ሦስቴ)፣ 3ሀ፣ 21ሐ
2. ዝማሬ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ፒል ተተኳሪ፣ መዝ. 135:3ለ
3. ባርኮት – ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ ፒል ተተኳሪ፣ መዝ. 135:19 (ሁለቴ)፣ 20 (ሁለቴ)

ለ. ያህዌ ይመሰገናል/ይባረካል/ይወደሳል፣ በ... ምክንያት
1. በባሕርዩ
   ሀ. እሱ መልካም ነው፣ መዝ. 135:3 መዝ. 147:1)
   ለ. እሱ ፍቅር /ተወዳጅ/ ነው፣ መዝ፣ 135:3 (መዝ. 27:4፤147:1)
   ሐ. እሱ ታላቅ ነው፣ መዝ. 135:5 (መዝ. 48:1፤145:3)
   መ. እሱ ከአማልክት በላይ ነው፣ መዝ. 135:5 (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት/በአንድ አምላክ ማመን)
   ሠ. ስሙ ለዘላለም ነው፣ መዝ. 135:13ሀ (ዘጸ. 3:15)
   ረ. ቃልኪዳኑን ማሰቡ እርግጠኛ ነው፣ መዝ. 135:13ለ
2. ለእስራኤል ያደረገው

ሀ. ያዕቆብን/እስራኤልን መረጠ፣ መዝ. 135:4 (ዘዳ. 7:6፤10:15)
ለ. ሉዓላዊ፣ መዝ. 135:6 (መዝ. 115:3፤መክ. 8:3፤ኢሳ. 46:8-10)
ሐ. ውኃን ተቆጣጥሯል፣ መዝ. 135:7 (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ውኆች)
መ. እስራኤልን ከግብፅ አድኗል፣ መዝ. 135:8-9 (መዝ. 136:10-15)
ሠ. እስራኤልን ጠብቋል፣ በመዞር ጊዜ፣ መዝ. 135:10-11 (መዝ. 136:16-22)

3. ለእስራኤል አድርጓል
ሀ. መረጣቸው፣ መዝ. 135:4
ለ. ፍርድን ሰጣቸው፣ መዝ. 135:14
(1) ስለ ኃጢአታቸው (ዕን. 10:26-31)
(2) ወይም ከእነርሱ ጎን ሆኖ በአሕዛብ ላይ (ዘዳ. 32:36)
ሐ. ግን ይቅር ይላል (ዘዳ. 32:26)

ሐ. ይህ መዝሙር የጣዖታትን ከንቱነት የሚያሳይ አንጓ ይጨምራል (መዝ. 135:14-18)፡፡ እሱ እና እሱ ብቻ ነው አምላክ (ልዩ ርዕስ ተመልከት: አሀዳዊነት)፡፡ ይህ አንጓ ከመዝ. 115:4-8 ጋር ተመሳሳይ ነው (ደግሞም ዘጸ. 20:23፤ዘዳ. 4:28፤29:17 ተመልከት)፡፡

መ. ብዙዎቹ/አብዛኞቹ የዚህ መዝሙር ሐረጋት በሌሎች የቅዱስ ቃሉ ጽሑፎች ላይ ይገኛሉ፡፡ የመዝሙሩ ጊዜ ርግጠኝነት የለውም /ማለትም፣ እሱ ጠቅሶ ነውን ወይስ ተጠቅሶ?/፡፡

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 135፡1-4**

**[1]ሃሌ ሉያ።**
**የእግዚአብሔርን ስም አመስግኑ**
**እናንተ የእግዚአብሔር ባሪያዎች ሆይ፥ አመስግኑት፥**
**[2]በእግዚአብሔር ቤት ውስጥ፥**
**በአምላካችን ቤት አደባባይ የምትቆሙ።**
**[3]እግዚአብሔር ቸር ነውና እግዚአብሔርን አመስግኑ**
**ለስሙ ዘምሩ፥ መልካም ነውና**
**[4]እግዚአብሔር ያዕቆብን ለራሱ፥**
**እስራኤልንም ለመዝገቡ መርጦታልና**

**135፡1ሐ-2** ይህ ሐረግ የሚጠቅሰው ካህናትን ነው፡፡ ሙሉውን ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 134፡1 ላይ፡፡

**135:1 "ሃሌ ሉያ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል "ሃሌ ሉያ" ነው፡፡ የእስራኤል አምላክ ስም በምሕጻረ-ቃል፣ ያህዌ - ያህ በሚል መጠቀሱን ተገንዘብ (መዝ. 135:1፣3፣4፣21)፣ ይኸውም የምስጋናው ማጠቃለያ የሚሆን /ሃሌ ሉያ/፡፡

▣ **"የእግዚአብሔርን ስም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት: "ስሙ" የያህዌ፡፡

**135:4 "እስራኤልን ለመዝገቡ"** እስራኤል የያህዌ ልዩ ምርጫ ነበር (ዘጸ. 19:5-6፤ዘዳ. 7:6፤14:2፤26:18፤ኢሳ. 43:21፤ሚል. 3:17፤1 ጴጥ. 2:9) ራሱን ለአሕዛብ ለመግለጥ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ/፡፡

**መዝሙር ፡ 135፡5-7**

**[5]እግዚአብሔር ታላቅ እንደ ሆነ፥**
**ጌታችንም ከአማልክት ሁሉ እንዲበልጥ አውቄአለሁና።**
**[6]በሰማይና በምድር በባሕርና በጥልቆች ሁሉ፥**
**እግዚአብሔር የወደደውን ሁሉ አደረገ።**
**[7]ከምድር ዳር ደመናትን ያወጣል**
**በዝናብ ጊዜ መብረቅን አደረገ**
**ነፋሳትንም ከመዛግብቱ ያወጣል።**

**135፡5 "አውቄአለሁና"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ፡፡

▣ **"ጌታ"** ይህ የዕብራይስጡ ሐዶን ሲሆን፣ ፍችውም "ጌታ፣" "ባለቤት፣" "ባል፣" ወይም "ጌታ" ማለት ነው፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፡፡

▣ **"ጌታችን ከአማልክት ሁሉ ይበልጣል"** ያህዌ ብቸኛው አምላክ ነው (ዘጸ. 18:11፤መዝ. 95:3፤96:4፤97:9፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት /በአንድ አምላክ ማመን/፡፡ ይህም የእስራኤል የማያካትት /የማይከፋፈል/ መሆን እጅግ ግልጽ የሆነበት ነው! እሷም ብቸኛዋ አሀዳዊ ሕዝብ ነች፣ ከጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/፡፡

**135:6 “በሰማይና በምድር በባሕርም”** ይህ የተለመደ ቋንቋ ነው፣ ለፍጥረት (ማለትም፣ ይህ ምድር፣ ዘጸ. 20፡11፤ነህ. 9፡6፤መዝ. 69፡34፤96፡11፤ 146፡6፤ሐጌ. 2፡6)፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማይ፡፡

▣ **“በባሕርና... በጥልቆች ሁሉ”** እነዚህ ተመሳሳዮች ይሆናሉ፣ በመጀመሪያ ያህዌ ከተቆጣጠራቸው /1/ የግብርና ውኃ እና /2/ ውኃን እንደ መሣርያ /ማለትም፣ መብረቅ፣ ጎርፍ፣ መቅሠፍቶች፣ ወዘተ/፡፡ ሁለተኛው የጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/ አፈ-ታሪክ ምናባዊ ምስያን የሚያመለክት ይሆናል፣ ያህዌ የውኃውን ሁከት ድል ያደረገበት (መዝ. 65፡5-7፤89፡9-10፤ኢዮብ 26፡12-13፤ኢሳ. 51፡9-10)፡፡

**137:7 “ከመዛግብቱ”** ይህ የዕብራይስጥ ስም ፍችው የሚሆነው “መዝገብ” ወይም “መጋዘን” ነው፡፡ ብኪ አዘውትሮ የአየር ሁኔታን ክስተት ምናባዊ ምስያ ይጠቀማል /ማለትም፣ የበረዶ ናዳ፣ በረዶ፣ ነፋስ፣ መብረቅ፣ ዝናብ/ጎርፍ/ በሰማያዊ መጋዘን የተጠበቀ፣ በያህዌ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ በበአል ሳይሆን፡፡

1. ዘዳ. 28፡12
2. ኢዮብ 38:22
3. መዝ. 33:7
4. ኤር. 10:13፤51:16

ያህዌ የተፈጥሮ ኃይላትን ይቆጣራል፣ ለራሱ ዓላማ (ሌዋ. 26:4-5፣9፣16፣19፣22፣26፤ዘዳ. 27:3፤28:4-5፣8፣11፣12፣17-18፣22፣24፣38-42)፡፡

## መዝሙር ፡ 135፡8-18

8የግብጽን በኵር ልጆች
ከሰው ጀምሮ እስከ እንስሳ ድረስ መታ።
9ግብጽ ሆይ፥ በመካከልሽ በፈርዖንና በባሪያዎቹ ሁሉ ላይ
ተኣምራትንና ድንቅን ሰደደ።
10ብዙ አሕዛብን መታ፥
ብርቱዎችንም ነገሥታት ገደለ።
11የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን፥
የባሳንንም ንጉሥ ዐግን፥
የከነዓንን መንግሥታት ሁሉ ገደለ
12ምድራቸውንም ርስት አድርጎ
ለእስራኤል ለሕዝቡ ርስት ሰጠ።
13አቤቱ፥ ስምህ ለዘላለም ነው፥
ዝክርህም ለልጅ ልጅ ነው
14እግዚአብሔር ለሕዝቡ ይፈርዳልና፥
ባሪያዎቹንም ይረዳልና።
15የአሕዛብ ጣዖታት የብርና የወርቅ፥
የሰው እጅ ሥራ ናቸው።
16አፍ አላቸው፥ አይናገሩምም
ዓይን አላቸው፥ አያዩምም
17ጆሮ አላቸው፥ አይሰሙምም
እስትንፋስም በአፋቸው የለም።
18የሚሠሩአቸው ሁሉ
የሚታመኑባቸውም ሁሉ እንደ እነርሱ ይሁን።

**135:8 “መታ”** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 645፣ ኬቢ 697፣ *ሂፊል የተጠናቀቀ*) የሚገልጸው አጠቃላይ ጥፋትን ነው፣ ከእግዚአብሔር የተላከና የተፈጸመ፡፡

1. መዝ. 135:8 – የያህዌ ከግብፅ የማውጣት ተስፋ (ዘፍ. 15:12-15፤ዘጸ. 3:20፤7:25፤9:15፤12:13፤መዝ. 87:4፤ኢሳ. 30:7)
2. መዝ. 135:10 – ያህዌ የከነአንን ሕዝቦች ማሸነፉ (ዘፍ. 15:16-21)

**135:13 “ለዘላለም”** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም /ኦላም/፡፡ ይህ የሥር ፍቺ ማቀያየር ሊሆን ይችላል፣ የያህዌ ከዕብራይስጥ ግሥ “የመሆን ግሥ፡፡” ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **“ዝክርህ”** |
| **አኪጀቅ፣ ጀፒኤስኦኤ** | **“ዝናህ”** |
| **አየተመቅ፣ የተእመቅ፣** | |
| **LXX** | **“ታዋቂነትህ”** |
| **አኢመቅ** | **“መታሰቢያህ”** |

የዕብራይስጡ ስም (ቢዲቢ 271) ፍችው “ዝክር” ወይም “መታሰቢያ” ነው፡፡

1. የሰዎች መታሰቢያ – ምሳ. 10:7፤መክ. 9:5
2. እስራኤል – ሆሴ.14:7
3. ያህዌ – ዘጸ. 3:15፤መዝ. 6:6፤30:4፤97:12፤102:12፤ኢሳ. 26:8፤ሆሴ. 12:5

**135:18** ጣዖታትን የሚያበጁና ከዚያም በኋላ የሚሰግዱላቸው እንደ እነርሱ ይሆናሉ፡፡
1. መናገር አይችሉም
2. ማየት አይችሉም
3. መስማት አይችሉም
4. መተንፈስ አይችሉም

እነርሱ ሕይወት-የለሽ ምናቦች ናቸው፣ የሐሰተኞች ሰዎች ልቦችና እጆች፡፡ ጣዖታት ሊረዱም ሊሰሙም አይችሉም፣ እንዲሁ ደግሞ የሚያመልኩአቸው!

**መዝሙር ፡ 135፡19-21**

**[19]የእስራኤል ቤት ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኩት።**
**የአሮን ቤት ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኩት**
**[20]የሌዊ ቤት ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኩት**
**እግዚአብሔርን የምትፈሩት ሆይ፥ እግዚአብሔርን ባርኩት።**
**[21]በኢየሩሳሌም የሚያድር**
**እግዚአብሔር ከጽዮን የተባረከ ነው።**
**ሃሌ ሉያ።**

**135፡19** ይህ የሚያመለክተው
1. ሁሉንም የእስራኤል ነገዶች
2. የተወሰኑትን የሌዊ ነገዶች፣ የአሮን ቤተሰብ፣ የያህዌ ምርጫ ለቤተ-መቅደሱ አገልጋዮች ከየት እንደሚሆኑ፡፡ ይህም ማለት፣ ይህ ነገድ የሁሉንም የያህዌ አገልጋዮች ነገዶች የበኩር ልጆችን ይተካል ማለት ነው /ዘጸአት 13/፡፡

**135:20 "የሌዊ ቤት"** ሌዋውያን ሁሉ ካህናት አልነበሩም፣ ነገር ግን ሁሉም ካህናት ከሌዊ ነገድ ነበሩ፡፡ አንዳንድ ሌዋውያን
1. በመቅደስ ያገለግላሉ /ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 134፡1/
2. በየአጥቢያው የሙሴ ሕግ መምህራን ነበሩ

▣ **"እግዚአብሔርን የምትፈሩ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፍርሃት፡፡

**135:21 "ጽዮን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሞሪያ፣ ጀቡስ፣ ሳሌም፣ ኢየሩሳሌም፣ ጽዮን፡፡

▣ **"በኢየሩሳሌም የሚኖር"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 132፡14 ላይ፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የእስራኤልን አምላክ ባሕርያት ዘርዘር፡፡
2. አሀዳዊነትን /በአንድ አምላክ ማንን/ ግለጽ፡፡
3. እግዚአብሔር ለዓላማው የአየር ሁኔታን ይቆጣጠራልን? ያ ማለት እግዚአብሔር ሁሉንም ማዕበል፣ ጎርፍ፣ እሳት ወዘተ. ይልካል ማለት ነውን?
4. በጣዖታት መታመን እጅግ የሚያሳዝነው ለምንድነው?

# መዝሙር 136
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጌታ ለእስራኤል ላለው መልካምነት ምስጋና<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | ምስጋና ለእግዚአብሔር ስለማያልቀው ምሕረቱ | ለጌታ ምስጋና ማቅረብ፣ ለሕዝቡ ስላደረገው ታላቅ ሥራ | የምስጋና መዝሙር | የአምልኮ ምስጋና |
| 136:1-9 | 136:1-3 | 136:1-3 | 136:1-3 | 136:1-3 |
| | 136:4-9 | 136:4-9 | 136:4-9 | 136:4-6 |
| | | | | 136:7-9 |
| 136:10-22 | 136:10-22 | 136:10-22 | 136:10-15 | 136:10-12 |
| | | | | 136:13-15 |
| | | | 136:16-22 | 136:16-20 |
| 136:23-26 | 136:23-25 | 136:23-25 | 136:23-25 | 136:21-24 |
| | 136:26 | 136:26 | 136:26 | 136:25-26 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

### ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. “ባርኩ” (ቢ.ዲቢ. 138፣ ኬቢ. 159፣ ፒል ተተኳሪS) መዝሙር 135ን እንደሚጀምርና እንደሚዘጋ ሁ፣ “አመስግኑ” (ቢ.ዲቢ. 392፣ ኬቢ. 389፣ ሂፊል ተተኳሪ) መዝሙ 136ን ይከፍታል ይዘጋልም፡፡

ለ. አምልኳዊው ተደጋጋሚ ፈርጅ በመዝሙሩ ላይ ግልጽ ነው፡፡ ራቢዎች እሱን “ታላቁ ሃለል” ብለው ይጠሩታል፡፡ ካህናት የእያንዳንዱን ቁጥር የመጀመሪያ ስንኝ ይላሉ እናም አምላኪዎችም /ምዕመናን/ ሁለተኛውን አዝማች ይላሉ፡፡

ሐ. መዋቅሩ/ሥነ-መለኮቱ የሚሆነው
1. ያህዌ ራሱ ባሕርዩ የተመለከተበት
2. የያህዌ የማዳን ሥራ ጎልቶ የተመለከተበት
3. ለእስራኤል ጥሪ የቀረበበት፣ ብሔራዊ አምላካቸውን፣ ብቸኛውን አምላክ እንዲያመሰግኑ

መ. መዝሙሩ ከመዝሙር 135 ጋር ትይዩ ነው

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 136፡1-9**

[1]**እግዚአብሔርን አመስግኑ ቸር ነውና፥**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።**

[2]የአማልክትን አምላክ አመስግኑ
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።
[3]የጌቶችን ጌታ አመስግኑ
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
[4]እርሱ ብቻውን ታላቅ ተኣምራትን ያደረገ
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
[5]ሰማያትን በብልሃት የሠራ
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
[6]ምድርን በውኃ ላይ ያጸና
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
[7]ብቻውን ታላላቅ ብርሃናትን የሠራ
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
[8]ለፀሐይ ቀንን ያስገዛው
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና
[9]ለጨረቃና ለከዋክብትም ሌሊትን ያስገዛቸው
ምሕረቱ ለዘላለም ነውና

**136፥1 "አመስግኑ"** *ግሡ* (ቢ.ዲ.ቢ. 392፣ ኬቢ. 389) *መሠረታዊ ፍችው "መወርወር" ወይም "መጣል" ማለት ነው፡፡ ሂፊል* ላይ ጥቅም ላይ የዋለው

1. ምስጋና ማቅረብ የአምልኮ ሐረጎችን በመዘመር
2. *መመስከር* (ሌዋ. 5:5፤ ምሳ. 28:13)

ኤቢ የሚለው አካላዊ የእንቅስቃሴ መኖሩን ነው፣ ምስጋና ከማቅረብ ጋር በተያያዘ፣ ይኸውም፣ ይህ ያልተያያዘ *ሥር* ጥቅም ላይ የዋለበት ምክንያት ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **"ቸር ነውና"** *የመጀመሪያው አንጓ /መዝ.* 136፡1-9/ *የሚገልጸው የያህዌን አካልና የፍጥረት ሥራዎቹን ነው፡፡*

1. ቸር ነውና (1 ዜና. 16:34፤ *መዝ.* 106:1፤107:1፤118:1፣29፤136:1፤ ኤር. 33:11)
2. እሱ ከአማልክት ሁሉ በላይ ነውና (ዘዳ. 10:17፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: አሀዳዊነት)
3. እሱ የምድር ፈጣሪ ነውና፣ *መዝ.* 136:4-9 (ዘፍጥረት 1፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት: ተአምራት ለመዝ. 136:4ሀ)

▣ **"ምሕረቱ ለዘላለም ነውና"** *ይህ ተደጋጋሚ ማረጋገጫ ነው የእግዚአብሔር ምሕረትና ዘላለማዊነት /በእያንዳንዱ ቁጥር ላይ ተደግሟል/፡፡*
"ምሕረት" ለሚለው ቃል ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት /*ሄሰድ*/፡፡ "ዘላለም" ለሚለው ቃል ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም /ኦላም/፡፡
ጠቃሚው የኪዳን ቃል *ሄሰድ* የተተረጎመባቸውን የተለያዩ መንገዶች ተገንዘብ /ቢ.ዲ.ቢ. 338/፡፡
1. አአመመቅ – "ምሕረት"
2. አኪጀቅ፣ LXX – "ምሕረት"
3. አየተመቅ፣ ጄፒኤስኦኤ – "ጽኑ ፍቅር"
4. አእቅ፣ የተእመቅ– "ፍቅር"
5. አኢመቅ – "ታማኝ ፍቅር"
6. አአመቅ – "የእግዚአብሔር ፍቅር"
7. አእት መጽሐፍ ቅዱስ – "የታመነ ፍቅር"

እንደማስበው፣ ይሄንን ቃል ለመግለጽ እጅግ የተሻለው መንገድ "የያህዌ ሁኔታዊ ያልሆነ፣ ታማኝ፣ የኪዳን ፍቅር ነው፡፡ እሱም ከሥነ-መለኮት አኳያ ከአኪ *ሊጋፔ* ጋር ይመሳሰላል፡፡

**136፡4 "እርሱ ብቻውን"** *ይህ የአሀዳዊነት ማረጋገጫ ነው፣ የእስራኤል የተለየነት፣ በጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/* (*መዝ.* 72:18፤ኢሳ. 44:24፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት: አሀዳዊነት)፡፡

▣ **"ታላቅ ተአምራትን"** LXX ቅጽሉን ይገድፈዋል፡፡ የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 417) ተከፋፍሏል፣ የትኛውን መቀበል እንደሚኖር፣ ኤምቲን ወይስ LXXን፡፡ "ታላቅ" የሚለው "ተአምራት" ከሚለው ጋር ይገኛል፣ ዘዳ. 6:22 ላይ፡፡

**136:5**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በጥበብ"** |
| **አኪጀቅ፣ አእቅ** | **"በጥበበ"** |
| **አየተመቅ** | **"በማስተዋል"** |
| **አኢመቅ፣ የተእመቅ** | **"በጥበብ"** |
| **ጄፒኤስኦኤ** | **"በጥበብ"** |

አንስታዩ ስም (ቢ.ዲ.ቢ. 108) ምሳ. 8:1 ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ ለእግዚአብሔር ቀዳሚ ፍጥረት፣ በእርሱም ሁሉን ነገር የፈጠረበት፡፡ ሌሎች ይህ ጥቅም ላይ የዋለባቸው ኢዮብ 26:12፤ምሳ. 3:19፤24:3፤ኤር. 10:12 ናቸው፡፡

ጽንሰ-ሐሳቡ "ተናገረ" ከሚለው ዘፍጥረት 1 ላይ ካለው ጋር ትይዩ ነው፡፡ እሱም የእግዚአብሔርን የፈጠራ ተግባራትን ያመለክታል፡፡

አኪ የሚያስረግጠው ኢየሱስ የእግዚአብሔር ወኪል መሆኑን ነው፣ በፍጥረት ላይ (ዮሐንስ 1:3፤10፤1 ቆሮ. 8:6፤ቆላ. 1:16፤ዕብ. 1:2)፡፡ የመጀመሪያዎቹ ሦስት ቁጥሮች፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ሥላሴን እንዴት እንደሚያካትቱ ተገንዘብ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሥላሴ/፡፡

1. ኤሎሂም /እግዚአብሔር/፣ ዘፍ. 1.1

2. ሩሕ /መንፈስ ቅዱስ/፣ ዘፍ. 1:2
3. እግዚአብሔር/ኢየሱስ አለ፣ ዘፍ. 1፡3፣6፣9፣14

**136፡6 "የዘረጋ"** ይህ ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 955፣ ኬ.ቢ. 1291) ይህ የሚያሳየው እግዚአብሔር የከባ አየርን ንፍቀ-ክበበ በምድር ላይ ማድረጉን ነው (ኢዮብ 37፡18፤ኢሳ. 42:5፤44:24፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማይ/፡፡

የቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ እንደሚለው ይህ ግሥ የሚያመለክተው እግዚአብሔር የብሱን/ደረቁን መሬት/ እና ውኆችን ማጽናቱን ነው /መዝ. 24፡2/፡፡ ይህ በርግጥ ይቻላል፡፡

**136፡7-9** እግዚአብሔር ብርሃናትን በሰማይ ላይ መፍጠሩ መጠቀሱ የአስትራን አምልኮ መቃወሚያ የዕብራውያን መንገድ ነው፡፡ ይህ ሥነ-መለኮታዊ ምናባዊ ምስያ ከግብፅ መቅሠፍቶች ጋር ይመሳሰላል /ዘጸአት 8-11/ የግብፅን የእንስሳት አምልኮ ከመቃወም ጋር፡፡ እግዚአብሔር፣ እና እሱ ብቻ ነው አምላክ! ሌላ ማንም የለም /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት/፡፡ "እርሱ ብቻውን" የሚለውን ተመልከት (ቢ.ዲ.ቢ. 94 II) መዝ. 136፡4ሀ ላይ፡፡

## መዝሙር ፡ 136፡10-22

[10]**ከበኵራቸው ጋር ግብጽን የመታ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[11]**እስራኤልንም ከመካከላቸው ያወጣ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[12]**በጸናች እጅ በተዘረጋችም ክንድ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[13]**የኤርትራን ባሕር በየክፍሉ የከፈለ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[14]**እስራኤልን በመካከሉ ያሳለፈ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[15]**ፈርዖንንና ሠራዊቱን በኤርትራ ባሕር የጣለ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[16]**ሕዝቡን በምድረ በዳ የመራ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[17]**ታላላቅ ነገሥታትን የመታ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[18]**ብርቱዎችንም ነገሥታት የገደለ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[19]**የአሞራውያንን ንጉሥ ሴዎንን**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[20]**የባሳንን ንጉሥ ዐግን**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[21]**ምድራቸውን ርስት አድርጎ የሰጠ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
[22]**ለባሪያው ለእስራኤል ርስት**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።**

**136፡10-22** መዝ. 136፡1-9 የፍጥረትን አምላክ ይገልጻል (ማለትም፣ ኤሎሂም፣ ዘፍጥረት 1)፤መዝ. 136:10-22 የሚገልጸው የመዳን/ብኪ. የደኅንነት አምላክን ነው /ማለትም፣ ያህዌ፣ ምንም እንኳ ባይጠቀስም በአንድምታ ተመልክቷል፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ደኅንነት [ብኪ.])፡፡

1. ተስፋ የተሰጠው ከግብፅ መውጣት/ዘጸአት /ዘፍ. 15፡12-15/
   ሀ. መቅሠፍቶች
   ለ. ቀይ/ሸምበቆ ባሕርን መከፋፈል /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቀይ ባሕር/
2. ተስፋ የተሰጠው ከነአንን ድል ማድረግ /ዘፍ. 15፡16-21/

**136:12 "በጸናች እጅ በተዘረጋችም ክንድ"** ይህ ሰውኛ ምናባዊ ምስያ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሲገለጽ) በብኪ. እጅግ የተለመደ ነው (ዘጸ. 13:3፣9፤6:1፤ዘዳ. 3:24፤4:34፤5:15፤6:21፤7:19፤26:8፤1 ነገ. 8:42፤ነሀ. 1:10፤መዝ. 44:3፣77:15፤ኤር. 32:21)፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡እጅ፡

**136፡13** ተመሳሳይ ቃላት ጥቅም ላይ ውለዋል፣ ዘጸ. 14፡27 ላይ፣ የግብፃውያንን ሠራዊት ጥፋት በመግለጽ፣ በቀይ/ሸምበቆ ባሕር ላይ፡፡

**136:21-22 "ርስት. . .ርስት"** ይህ ስም (ቢ.ዲ.ቢ. 635) ይህ ምናባዊ ምስያ የተገኘው ከእስራኤል የተለየ ስፍራነት ነው፣ እንደ ያህዌ የተለየ ምርጫ /መዝ. 135፡4 ተመልከት/፡፡

1. ከነአንን ሰጣቸው፣ ለአብርሃም የሰጠውን ተስፋ ለመፈጸም (ዘፍ. 15:12-21)፡፡ ይህም ዳግመኛ ተመልክቷል፣ ዘዳግም (ዘዳ. 4:21፤15:4፤ 19:10፤20:16፤21:28፤24:4፤25:19፤26:1 ላይ)፡፡
2. ለእያንዳንዱ የእስራኤል ነገድ የየራሳቸውን ርስት ምድብ ሰጣቸው (ኢያሱ 13-19)፡፡

3. እስራኤል የያህዌ ልዩ ርስት ነበር፣ ከሌሎቹ አሕዛብ ሁሉ (ዘዳ. 4:20፤7:6፤9:26፣29፤32:9፤1ነገ. 8:51፤መዝ. 28:9፤33:12፤78:62፣71፤ 94:5፣14፤106:40)፡፡

**መዝሙር ፡ 136፡23-26**

**[23]እኛን በመዋረዳችን አሰበናልና**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
**[24]ከጠላቶቻችንም እጅ አድኖናልና**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና**
**[25]ለሥጋ ሁሉ ምግብን የሚሰጥ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።**
**[26]የሰማይን አምላክ አመስግኑ**
**ምሕረቱ ለዘላለም ነውና።**

**136፡23-26** ይህ አንጓ የእግዚአብሔርን ታላቅ ሥራዎች ያጠቃልላል፣ ለእስራኤል ያደረገውን፣ ብሎም የእርሱን ሥራ ለሰው ሕይወት ሁሉ መጋቢነቱን (መዝሙር 104:27-30፤145:15፤ማቴዎስ 5:45፤ሐዋ. 14:17)፡፡ ይህም የስሞቹን ፍችዎች ያደባልቃል፡፡

1. ኤሎሂም - ፈጣሪ፣ መጋቢ፣ ደጋፊ
2. ያህዌ - አዳኝ፣ ታዳጊ፣ ኪዳን ሰጭ አምላክ

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፡፡

**136:23 "በመዋረዳችን"** ይህ የሚጠቅሰው ርግጠኝነት የለውም

1. የመሳፍንት ዘመንን
2. በግብፅ ባርነትን
3. ግዞት በሜሶፖታሚያ

**136:26 "የሰማይ አምላክ"** ይህ ኋላ ላይ ዞሮአስትራዊ የእግዚአብሔር መጠሪያ ነው፣ እሱም በድኅረ-ግዞት ዘመን እጅግ የተለመደ፡፡ አይሁድ ዘወትር የአምልኮተ-ባዕድ ጣዖታትን ስም እና የባዕዳንን ገዥዎች መጠሪያ ገላጭ ሐረጎች ለያህዌ መግለጫ ይወስዳሉ፡፡

ሰማይ የብዙ ቁጥር ነው፣ እንደ ብዙዎቹ የዕብራይስጥ ቃላት ታላቅነትን ለመግለጽ፡፡ ራቢዎች ዘወትር ያብራራሉ፣ ምን ያህል የሰማይ ደረጃዎች በዕብራይስጥ መጽሐፍ ቅዱስ እንደተጠቀሰ፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማይ እና ሦስተኛው ሰማይ፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "ያህዌ መልካም ነው" ማለት ምን ማለት ነው?
2. "ምሕረት" እጅግ ጠቃሚ የሆነ ሥነ-መለኮታዊ ቃል የሆነው ለምንድነው?
3. መዝ. 136፡1-4 አሀዳዊነትን /በአንድ አምላክ ማመንን/ በግልጽ ያብራራልን?
4. መዝ. 136፡6 የሚያመለክተው ምን ሁነት ነው?
5. ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ እና ከዋክብት እንደ እግዚአብሔር ፍጥረት ለምን ተጠቀሱ?
6. ቀይ ባሕር የት ነው?
7. ዘፍጥረት የቱጋ ነው ድሉ የተተነበየው?
8. መዝ. 136፡25 የቱን የእግዚአብሔር ባሕርይ ነው የሚጠቅሰው?

# መዝሙር 137
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የምርኮኝነት ተሞክሮ<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | ጽዮንን ማሰብ በባዕድ ምድር | ጸሎት በእስራኤል ጠላቶች ላይ ለበቀል /ሰቆቃ/ | የእስራኤላውያን ሰቆቃ በግዞት ላይ | የግዞት መዝሙር |
| 137:1-3 | 137:1-3 | 137:1-3 | 137:1-3 | 137:1-2 |
| | | | | 137:3 |
| 137:4-6 | 137:4-6 | 137:4-6 | 137:4-6 | 137:4-5 |
| | | | | 137:6 |
| 137:7-9 | 137:7-9 | 137:7-9 | 137:7 | 137:7 |
| | | | 137:8-9 | 137:8-9 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡ 137፡1-3**

**[1]በባቢሎን ወንዞች አጠገብ**
**በዚያ ተቀመጥን**
**ጽዮንንም ባሰብናት ጊዜ አለቀስን።**
**[2]በአኻያ ዛፎችዋ ላይ**
**መሰንቆቻችንን ሰቀልን።**
**[3]የማረኩን በዚያ የዝማሬን ቃል ፈለጉብን፥**
**የወሰዱንም።**
**የጽዮንን ዝማሬ ዘምሩልን አሉን።**

**137:1 "በባቢሎን ወንዞች አጠገብ"** የተሻለ ትርጉም ሊሆን የሚችለው "በውኃ መፋሰሻዎች" ነው፡፡ የዛን ጊዜው የባቢሎን የውኃ ሥርዓት ወንዞችን ብቻ አልነበረም የሚያካትተው፣ ሰው ሠራሽ ቦዮችንም እንጂ፣ እንደ ቼባር ቦይ ያለው /ሕዝ. 1፡1/፡፡
ከሐዋ 16፡13 እንደምንረዳው የጥንት ልማድ ነው፣ ምኩራብ የሌላቸው ከተሞች በአካባቢው ወንዝ ዳር ለአምልኮ መሰባሰብ፡፡ ይህም ጉዳይ እዚህጋ ሊሆን ይችላል፡፡

▣ **"እዚያም ተቀምጠን አለቀስን"** "መቀመጥ" እና "ማልቀስ" ከሚሉት ቃላት መደባለቅ የተነሣ ይህ ይህ ከቀብር ሙሾ መቼት ጋር የሚያያዝ ይመስላል፡፡ ምድር ላይ እግርን ዘርግቶ መቀመጥ የአይሁድ የኀዘን መለያ ነው፡፡

▣ **"ጽዮንን አሰብናት"** አስገራሚ የሚሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ሰዎች ማሰባቸው /ማስታወሳቸው/ ጠቃሚ መሆኑ ነው /መዝ. 137፡5 [በአንድምታ]፣6፣7)፡፡ "ከፍ ማለት" የሚለው ቃል መዝ. 137:6 በአይሁድ የኅትመት ሶሳይቲ በአሜሪካ፣ በአዲሱ ትርጉማቸው ላይ የተተረጎመው "ኢየሩሳሌምን ሳላቋርጥ ማሰቤ የደስታ ሰዓቴ ነው" በሚል ነው፡፡

"ጽዮን" የሚለው ቃል ለሞላው የኢየሩሳሌም ከተማ እና ለመቅደሱ አካባቢ፣ ይኸውም በሞሪያ ተራራ ላይ ለተተከለው ተመሳሳይ ነው /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሞሪያ፣ ሳሌም፣ ኢየሩሳሌም፣ ጽዮን/፡፡ ለእኛ እጅግ አስቸጋሪ ነውሙሉውን የእስራኤል ግዞት አንድምታ ለመረዳት፡፡ እርሷ ዘላለማዊ የሆነ ዳዊታዊ ንጉሥ ቃል ተገብቶላታል (2 ሳሙ. 7፡10፣13፣16)፡፡ እሷም ከሶርያ ንጉሥ ከሰናከሬ ወረራ ተጠብቃለች፣ በሕዝቅያስ ዘመን /ኢሳይያስ 37/፡፡ ሆኖም፣ ኤርምያስ ነግሯቸው ነበር፣ ስደቱ ሊመጣ እንደሚችል፣ ንስሐ ገብተው ወደ እግዚአብሔር እስካልተመለሱ ድረስ፡፡ ኪዳኑ /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኪዳን/ ዘወትር ሁኔታዊ ነበር (1 ሳሙ. 13፡12፣13)፣ ነገር ግን እነርሱ በጥንቱ ወግ ተራመዱ ግላዊ ግንኙነትን ከማድረግ ይልቅ፡፡ ስለዚህ፣ የእግዚአብሔር ኪዳን እንዳይሠራ ተደረገ /ማለትም፣ ስደት/ በእነርሱ ጊዜ፡፡

**137፡2 "አኻያ ዛፍ"** የግብርና ባለሙያዎች እንደሚነግሩን አኻያ ዛፍ በጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/ አያድግም፣ ነገር ግን ይህ ዛፍ /ቢ.ዲ.ቢ 788 II) የታወቀ ዛፍ ሊሆን ይችላል በኤፍራጥስ እና ዮርዳኖስ ወንዞች ዳርቻ የሚበቅል፡፡ ዩቢኤስ፣ *የመጽሐፍ ቅዱስ ፉና እና ፍሎራ ተመልከት*፣ ገጽ 170፡፡ አንዳንዶች ይልቁንም የሚሉት የዚህ ልዩ ዛፍ ቅርንጫፍ የዳስ በዓል ጊዜ ጥቅም ላይ ይውል ነበር፣ ሰዎች የሚያርፉበትን ዳስ /መጠለያ/ ለማዘጋጀት፡፡

▣ ***"መሰንቆቻችንን ሰቀልን"*** አስገራሚ የሚሆነው፣ መዝ. 137፡1-3 ላይ ያሉት ግሦች ሁሉ የተጠናቀቁ ጊዜያት መሆናቸው ነው፣ ይህም ምናልባት የሚያመለክተው ደራሲው በሆነ ወቅት ከስደቱ ወዲህ ወደ ኋላ ላይ እንደኖረና ስላለፈው መራራ ተሞክሮ እንደ ጻፈ ነው፡፡

የተመቀ "መሰንቆ" የሚለውን ቃል የሚተረጉመው (ቢ.ዲ.ቢ 490) "በገና" በሚል ነው፡፡ ይህም እጅግ አስቸጋሪ ያደርገዋል፣ የትኛው ዓይነት የሙዚቃ መሣርያ ጥቅም ላይ እንደ ዋለ፣ ምክንያም ስሞቹ ከባህል ወደ ባህል ስለሚለዋወጡ፣ የመሣርያዎቹ ንድፍ ላይ እንደሚደረገው፡፡ እሱ አነስተኛ የጅማት/ገመድ የሙዚቃ መሣርያ ነው፡፡

**137፡3 "እዚያም የማረኩን… የወሰዱንም"** በአንዳንድ አታቾች/ኮሜንታተርስ የሚሉት ይህ ቁጥር በባቢሎናውያን ማራኪዎች የተደረገ ስልቂያ/መሳለቅ ምሳሌ ነው፣ ነገር ግን በአመመቅ ቃሉ ሲተረጎም "ፈለጉብን" የሚል ነው፣ በእውነታው እጅግ ቀለል ያለው የዕብራይስጥ ቃል "ጠየቁን" (ቢ.ዲ.ቢ 981፣ ኬቢ 1371፣ *ቃል የተጠናቀቀ*)፡፡ እሱም ፍጹም ሊሆን የሚችለው ባቢሎናውያን እጅግ የሚፈልጉት አዲስ ዓይነት ዜማ ነበር፣ አይሁድ የሚያወጡት፡፡ ሆኖም፣ አይሁድ ሃይማኖታዊ ዝማሬዎችን በባዕድ ምድር መዘመር አይችሉም፣ ምክንያቱም እነርሱ እነርሱ ለያህዌ አምልኮ የተገቡ ስለሆኑ፣ እሱም በማድርከ የተሸነፈ የመሰለ፡፡ ይህ ለአይሁድ እጅግ ግራ የመጋባት ጊዜ ነው፣ በዚህ የታሪክ ዘመን፡፡ በጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/ ጽንሰ ሐሳብ አለ፣ ማንም በጦርነት ድል ያደረገ በብሔራዊ አምላኩ ኃይል እንዳገኘ ይቆጠራል፡፡ ያህዌ ስለ ራሱ ስም ፍቃደኛ ሆነ እንዲቃረኑት፣ ሕዝቡ እሱን ወደ ማመን ይመለስ ዘንድ፡፡

▣ በሠ የሚጀምሩ በርካታ ቃላት መኖራቸውን ተገንዘብ፡፡

1. መዝ. 137:3 ግስ፣ "መጠየቅ" – ቢ.ዲ.ቢ 981፣ ኬቢ 1371፣ *ቃል የተጠናቀቀ*
2. መዝ. 137:3 አንቀጽ፣ "ማራኪዎች" – ቢ.ዲ.ቢ 985፣ ኬቢ 1382፣ *ቃል አንቀጽ*
3. መዝ. 137:3 ስም፣ "ዝማሬዎች" – ቢ.ዲ.ቢ 1010
4. መዝ. 137:3 ስም፣ "መሳለቂያ" – ቢ.ዲ.ቢ 970
5. መዝ. 137:3 ግሥ፣ "ዝማሬ" – ቢ.ዲ.ቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ *ቃል ተተኳሪ*
6. መዝ. 137:4 ስም፣ "ዝማሬዎች" – ቢ.ዲ.ቢ 1010
7. መዝ. 137:4 ግሥ፣ "መዝሙሮች' – ቢ.ዲ.ቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
8. መዝ. 137:4 ስም፣ "መዝሙር" – ቢ.ዲ.ቢ 1010
9. መዝ. 137:5 ግሥ፣ "መርሳት" – ቢ.ዲ.ቢ 1013፣ ኬቢ 1489፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ*
10. መዝ. 137:5 ግሥ፣ "መርሳት" – ቢ.ዲ.ቢ 1013፣ ኬቢ 1489፣ *ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
11. መዝ. 137:6 ስም፣ "ደስታ" – ቢ.ዲ.ቢ 970

▣ ***"የወሰዱን"*** ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ 1064፣ ኬቢ 1700) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፡፡ እሱም ሊሆን የሚችለው

1. ከ"ጠላፊዎቻችን" ጋር ትይዩ፣ መዝ. 137:3ሀ
2. "የወሰዱን" (የተእመቀ)፣ LXX፣ ፔሺታ፣ ቫልጌት
3. ከሌላ የዕብራይስጥ ሥር ( ַלַה – ቢ.ዲ.ቢ 237)፣ "ያፌዙብን"

## *መዝሙር ፡ 137፡4-6*

**[4]የእግዚአብሔርን ዝማሬ**
**በባዕድ ምድር እንዴት እንዘምራለን?**
**[5]ኢየሩሳሌም ሆይ፥ ብረሳሽ፥**
**ቀኜ ትርሳኝ።**
**[6]ባላስብሽ፥**
**ምላሴ በጒሮሮዬ ይጣበቅ**
**ከደስታዬ ሁሉ በላይ**
**ኢየሩሳሌምን ባልወድድ።**

**137:4 "የእግዚአብሔርን ዝማሬ**

**በባዕድ ምድር እንዴት እንዘምራለን?"** አንዳንዶች ይሄንን መግለጫ የሚያያይዙት ከብሔራዊ አማልክት ጽንሰ-ሐሳብ ጋር ነው፣ ለእኔ እንደሚመስለኝ ግን እሱ የሚያመለክተው ከመዝሙራቱ ሃይማኖታዊ ባሕርይ አኳያ ነው፣ እናም የያህዌን ዝማሬ በዚህ ፍርድና መነጠል መካከል መዘመር እንደማይቻል ነው፡፡ ርግጠኛ ነኝ፣ አይሁድ በርግጥ ተደንቀዋል፣ የእግዚአብሔር ኪዳን ለዘላለም የተሰበረ እንደሁ፣ ዳግመኛም ፈጽሞ ከወደዳቸው፣ እናም ለሕዝባቸው አንዳች ተስፋ ካለ፡፡ እግዚአብሔር እነዚህን ጥያቄዎች በቀና መንገድ ነው በመጪው ጊዜ የሚመልሰው፣ ነገር ግን በዚህ ጊዜና ሰዓት ታላቅ መደነጋገርና ያለመገንዘብ አለ፡፡

▣ **"የጌታ"** ይህ ያህዌ ነው፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፡፡

**137፡5 "ኢየሩሳሌም ሆይ፣ ብረሳሽ"** ይህ የሚያሳየው እምነታቸውን ነው፣ በጨለማ ጊዜ መካከል፡፡ መዝሙር 137፡5-6 የራስ መሐላ ነው፣ ለነገሩ ጽኑዕነት ጥቅም ላይ የሚውል!

▣ **"<u>ብ</u>ረሳሽ... <u>ባ</u>ላስብሽ"** እነዚህ ሁለቱ ቃል ያልተጠናቁ ናቸው፣ በተጽዕኖዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ፡፡

▣ **"ቀኜ ትርሳኝ"** "ጥበብዋን" የሚሉት ቃላት በኢታሊክ/አግድም መጻፋቸውን ተገንዘብ፣ አአመመቅ ላይ፣ ይህም ማለት ኤምቲ ላይ የሉም ማለት ነው፡፡ ምክንያቱም ዐውደ-ጽሑፉ ዝማሬ በመሆኑ፣ ይህ የሐቂ ጠቃሽ ሊሆን ይችላል፣ ማለትም እነዚህ የአይሁድ ሙዚቀኞች ሃይማኖትን እንደ ካደ ይሆናሉ፣ ሃይማኖታዊ ዝማሬዎችን በምርኮ ላይ በመዘመር፣ እናም የሙዚቃ ችሎታቸውን አጥተው ሊሆን ይችላል፣ እንደ ሙዚቀኛ፡፡ ይህም የመዝ. 137፡6 አጽንዖት ሊሆን ይችላል፣ የመዘመር ችሎታን ማጣት አንድምታ፡፡

**137፡6 "ከደስታዬ ሁሉ በላይ**
**ኢየሩሳሌምን ባልወድድ።"** ጥሬአዊው ሐረግ፣ "ከራስ በላይ፣" የተለየ ነው፣ እናም አምልኳዊ የአካል ምልክትን የሚገልጽ ይመስላል ወይም ተምሳሊታዊ የራስ ሽፋን፡፡ LXX "ራስ"ን እንደ "መጀመሪያ" ወይም "መነሻ" አድርጎ ይወስደዋል /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ራስ/፡፡
በእነዚህ ያልተለመዱ ቅኔአዊ ቃላት እጅግ እንደሚዘወተረው፣ ማስታወስ እጅግ የተሻለ የሚሆነው

1. ትይዩው ፍንጭ እንደሚሰጠን ነው
2. የተጓዳኝ ቃሉ ሥሮች ሥርወ-ቃል ዘወትር የፍችው አመላካች ነው
3. የመዝሙሩ አጠቃላይ ግፊት

ጀፒኤስኦኤ "ኢየሩሳሌምን ማሰቤ የደስታ ሰዓቴ ነው" የሚል አለው፡፡

---

**መዝሙር ፡ 137፡7-9**

**7 አቤቱ፥ በኢየሩሳሌም ቀን**
**የኤዶምን ልጆች አስብ።**
**እስከ መሠረትዋ ድረስ**
**አፍርሱ አፍርሱ ያሉአትን።**
**8 አንቺ ወራዳ የባቢሎን ልጅ ሆይ፥**
**ስለ ተበቀልሽን የሚበቀልሽ የተመሰገነ ነው።**
**9 ሕፃናቶችሽን ይዞ በዓለት ላይ የሚፈጠፍጣቸው የተመሰገነ ነው።**

---

**137፡7 "አቤቱ፣ ጌታ፣ የኤዶምን ልጆች አስብ"** ሰዎች የእግዚአብሔርን ጸጋ ማስታወስ እንደሚገባቸው፣ እግዚአብሔር የእስራኤልን ኃጢአት ለመርሳት ዝግጁ ነው (ቃል ተተኳሪ በጸሎት ጥቅም ላይ የዋለ) እግዚአብሔር ሲያስታውሰው ዘወትር ከፍርድ አኳያ ነው፡፡ ያም በትክክል የዚህ ዓረፍተ-ነገር ዓላማ ነው፣ እግዚአብሔር የበቀል አምላክ ነው፣ ዘዳ. 32፡35፣ በፍትሐዊነትና በትክክል ያደርጋል፣ በኤዶም ልጆች ላይ፣ እነርሱም በገዛ ዘመዶቻቸው ላይ ግፍ የፈጸሙ /ማለትም፣ አይሁድ/፡፡ በርካታ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ማስረጃዎች አሉ፣ ኤዶም በኢየሩሳሌም ከበባ፣ ውድቀት፣ እና ውድመት ላይ ለመሳተፉ (መዝ. 87:4-8፤ኤር. 49:7-22፤ሰቆ. 4:21፤ሕዝ. 25:12-14፤35:1፤አሞጽ 1:11፤ኢዩኤል 3:19፤እና በተለይ አብድዩ 10-14)፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ኤዶም እና እስራኤል፡፡

▣ **"አፍርሱ አፍርሱ ያሉአትን።"** ይህ ታሳቢ ቃል ነው /ሁለት ፒይል ተተኳሪዎች/ የኤዶማውያን፣ ኢየሩሳሌም በናቡከደነፆር ሠራዊት ስትፈርስ፡፡ ሆኖም፣ የአይሁድ ኅትመት በአሜሪካ አዲሱ ትርጉም፣ "ራቁቷን አስቀሯት፣ ራቁቷን አስቀሯት" የሚል አለው፡፡ ይህም ፍጹም ሊሆን የሚችል ነው፣ ኢሳ. 47:2-3፤ሰቆ. 1:8፤ሕዝ. 16:37፡፡ እዚህጋ ያለው ዘይቤ በሕዝብ ፊት እንድታፍር የተደረገች ሴት ነች፡፡ ይህ ትርጓሜ በቀጣዩ ሐረግ እውነታ ይጠናከራል፣ "እስከ መሠረትዋ ድረስ፣" "መቀመጫ" ተብሎ ሊተረጎም ይችላል (ቢዲቢ 414፣ ኬቢ 417፣ ኤቢ፣ ገጽ 273)፡፡ እኔ እንደማስበው የመጀመሪያው አማራጭ የተሻለ ነው፡፡

**137:8 "የባቢሎን ልጅ ሆይ"** እጅግ የተለመደ ነው ሕዝቦችን "ሴት ልጅ" ብሎ መጥራት፡፡ ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ሞላውን ሕዝብ ለማካተት ጥቅም ላይ የዋለ፡፡ ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት ኤር. 46፡11 ላይ፣ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር፡፡ አስገራሚ የሚሆነው የመዝ. 137፡8 ሦስቱ ግሦች ኤር. 51፡56 ላይ መደገማቸው ነው፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"አንቺ የተደመሰስሽ"** |
| **አኪጀቅ** | **"አንቺ የወደምሽ"** |
| **አየተመቅ፣ አአመመቅ ኅዳግ** | **"አንቺ ደምሳሽ"** |
| **አእቅ** | **"ትደመሰሻለሽ"** |
| **አኢመቅ** | **"በጥፋት ታበቂያለሽ"** |
| **ጀፒኤስኦኤ፣ ታርጉምስ** | **"አንቺ አውሬ"** |
| **የተእመቅ** | **"አጥፊ"** |

ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት፣ ገጽ 419፣ "አንቺ የተደመሰስሽ" ለሚለው "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል /መጠነኛ ጥርጣሬ/፡፡ በአማራጮቹ መካከል ያሉት ልዩነቶች

1. הַהדוּשָׁה – አንቺ የተደመሰስሽ

2. דדהשׂה – አንቺ ደምሳሽ

▣ **"ስለ ተበቀልሽን የሚበቀልሽ የተመሰገነ ነው።"** ይህ የብኪ ምሳሌ ነው፣ "ዓይን ስለ ዓይን" ለሚለው ፍርድ፣ የሌዋ. 24፡19-22፤ ዘዳ. 19፡19፤ እሱም በኤርምያስ 51 ላይ የተደገመ፡፡ የዘራነውን እናጭዳለን /ዘወትር "ሁለቱ መንገዶች" ተብሎ ይጠራል፣ ኢዮብ 34፡11፤መዝ. 28:4፤62:12፤ምሳ. 24:12፣29፤መክ. 12:14፤ኤር. 17:10፤32:19፤ማቴ. 16:27፤25:31-46፤ሮሜ. 2:6፤14:12፤1 ቆሮ. 3:8፤2 ቆሮ. 5:10፤ገላ. 6:7፤2 ጢሞ. 4:14፤1 ጴጥ. 1:17፤ ራዕ. 2:23፤20:12፤22:12)፡፡

ስድስት የከፉ ርግማን (ማለትም፣ ርግማን) መዝሙራት አሉ፣ ማለትም፣ መዝሙር 55፤59፤69፤79፤109፤137፡፡

**137:9 "ሕፃናቶችሽን የሚፈጠፍጥ"** ይህ የተለመደ ተግባር ነው፣ በጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/ (2 ነገ. 8:12፤ኢሳ. 13:16፣18፤ሆሴዕ 10:14፤ናሆም 3:10)፡፡ መገንዘብ አስገራሚ የሚሆነው ተመሳሳይ ትንቢት ኢሳ. 13:16 ላይ ለባቢሎን መጠቀሱ ነው፡፡ ይህም አስፈሪ ምሳሌ ነው፣ የዘራነውን ለምናጭደው ሐቅ፡፡ ታሪክ ጸሐፊው ፕሪዲዩክስ፣ እንደሚነግረን ባቢሎን በከበባ ውስጥ በወደቀችበት ጊዜ ሴቶችና ሕፃናት ይገደሉ ነበር፣ ብዙ ምግብ ለማስቀረት፣ ለከተማው ወታደራዊ ኃይል፡፡

▣ **"ዓለት"** ስሙ /ቢ.ዲ.ቢ 700/ የተወሰነ አንቀጽ/ግሥ አለው፡፡ የሚያመለክተውም

1. የፔትራ ስም /ዘወትር "ቀዩ" ከተማ ተብሎ የሚጠራ/፣ የኤዶም ዋና ከተማ (ቢ.ዲ.ቢ. 701፣ 2 ነገ. 14:7)
2. ጣዖት አምላኪነትን የማሳያ መንገድ፣ እሱም የያህዌ ተቃራኒ፣ "እውነተኛው ዓለት"
3. አንዳንዶች ቃሉን ያርሙታል "አራም" በሚል /አገር/
4. ጠንካራ ገጽታን መግለጫ መንገድ፣ እንደ ግንብ ወይም የቤት ጎን፡፡ ይኸም ከዐውደ-ጽሑፉና ከትይዩው ጋር በተሻለ ይገጥማል፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. የባቢሎን ምርኮ ለምን ይሄን ያህል ሥነ-መለኮታዊ ቀውስ ሆነ?
2. እነዚህ በእስራኤል ሕዝብ ሕይወት ላይ የሆኑ ምሳሌዎች፣ በእኛ በቤተ-ክርስቲያን ላይ እንዴት ሊገበሩ ይችላሉ?
3. "መርሳት" እና "ማስታወስ" የሚሉትን ቃላት አብራራ፣ እንዴት አድርገውም በብኪ መቼት ጥቅም ላይ እንደሚውሉ፡፡
4. አንዱ ጥንታዊውን የጦርነት ልምምዶች፣ ከሞራል አኳያ ከእኛ ከራሳችን ዘመናዊ ልምምዶች ጋር እንዴት ማነጻጸር ይችላል?

# መዝሙር 138
## የአዲሶቹ ትርጕሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእት | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ምስጋና ማቅረብ ለጌታ ውዴታ ኤምቲ መግቢያ የዳዊት መዝሙር፡፡ | የጌታ መልካምነት ለታማኝ | ምስጋናና ከችግር መዳን | ምስጋና የማቅረብ ጸሎት | ምስጋና የማቅረብ ዝማሬ |
| 138:1-3 | 138:1-3 | 138:1-3 | 138:1-3 | 138:1-2ሀ |
| | | | | 138:2ለ-3 |
| 138:4-6 | 138:4-6 | 138:4-6 | 138:4-6 | 138:4-6 |
| 138:7-8 | 138:7-8 | 138:7-8 | 138:7-8 | 138:7-8 |

### የንባብ ምድብ ሦስት (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ ቁጭታ አንብበው። ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ዑደት ቁ. 3፣ ገጽ xvi)። ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ። ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል። እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል።

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፤ 138፥1-3**

**1አቤቱ፥ በፍጹም ልቤ አመሰግንሃለሁ፥**
**የአፌን ነገር ሰምተኸኛልና በመላእክት ፊት እዘምርልሃለሁ።**
**2ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ**
**ስለ ምሕረትህና ስለ እውነትህ ስምህንም አመሰግናለሁ፥**
**በሁሉ ላይ ቅዱስ ስምህን ከፍ ከፍ አድርገሃልና።**
**3በጠራሁህ ቀን በፍጥነት አድምጠኝ**
**ነፍሴን በኃይልህ በብዙ አጸናሃት።**

**138፥1-3** ይህ አንጓ መዝሙረኛው ሊያደርግ ያለውን ዋና ነገሮች ዝርዝር ይዟል /አራት ያልተጠናቀቁዎች፣ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ/፣ መዝ. 138፥4-6 ደግሞ አሕዛብ ማድረግ የሚኖርባቸውን ያንጸባርቃል፡፡

1. አመሰግንሃለሁ – ቢዲቢ 392፣ ኬቢ 389፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ምስጋና እዘምርልሃለሁ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ *ፒል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. ወደ ቅዱስ መቅደስህ እሰግዳለሁ – ቢዲቢ 1005፣ ኬቢ 295፣ *ሂሽታፌል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
4. ምስጋናን አቀርባለሁ - ከቁ. 1 ጋር ተመሳሳይ

ያህዌ በጸለየበት ጊዜ ሰምቶታል/ምላሽ ሰጥቶታል፣ እናም መስማቱን ቀጥሏል፣ ምክንያቱም

1. እሱ ታማኝ ተከታይ በመሆኑ፣ በያህዌ የተበረታታና የተጠናከረ፣ መዝ. 138፥3ለ
2. ከያህዌ ባሕርይ የተነሣ
   ሀ. ስሙ፣ መዝ. 138:2ለ፣ሐ
   ለ. ምሕረቱ፣ መዝ. 138:2ለ
   ሐ. ታማኝነቱ፣ መዝ. 138:2ለ

መ. ቃሉ፣ መዝ. 138:2ሐ

የ "ኬ" ድምጽ ምን ያህል ጊዜ ቃላቱን እንደሚዘጋ ተገንዘብ፣ መዝ. 138፡1-2 ላይ፡፡

1. አመሰግንሃለሁ፣ መዝ. 138:1
2. ምስጋናህን እዘምራለሁ፣ መዝ. 138:1
3. ቅዱስ፣ መዝ. 138:2
4. ስምህ፣ መዝ. 138:2
5. ምሕረትህ፣ መዝ. 138:2
6. እውነትህ/ታማኝነትህ፣ መዝ. 138:2
7. ስምህ፣ መዝ. 138:2
8. ቃልህ፣ መዝ. 138:2

**138:1 "በፍጹም ልቤ"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ለፍጹም መሰጠት (መዝ. 86:12፤111:1)፡፡ ይህ ልዩነቱን ማሳያ መንገድ ነው በእምነት/በታማኝነት አኳያ

1. ዳዊት - በልቡ ሁሉ /ከቤርሳቤህ በፊትና ኋላም ከአስፈሪው ተከታታይ ሁኔታ በኋላ/
2. ሰሎሞን - የተከፋፈለ ልብ /በሽመገለ ሰዓት/

ጉዳዩ ኃጢአት አይደለም፣ ሁሉም ኃጢአትን ሠርተዋል /መዝ. 130፡3-4 ላይ ማስታወሻ ተመልከት/፣ ነገር ግን ቀጣይነት ያለው እምነት እና ንስሐ፡፡ ከያህዌ ጋር ያለ ግንኙነት ቁልፍ ነገር ነው፣ በሰው ጥረት ላይ የተመሠረተ ሥራ ሳይሆን፡፡

▣ **"በመላእክት ፊት"** ይህ በሁለት መንገዶች ሊታይ ይችላል፡፡

1. በሰማይ የዙፋኑ ክፍል /ማለትም፣ የመቅደስ አምልኮ/ እዚያም መዝሙረኛው የእምነት መዝሙሮቹን የሚያቀርብበት /ማለትም፣ ሰማያዊ ጉባኤ፣ መዝ. 82:1፤89:7-8፤95:3፤96:4፤97:9)
2. ያህዌ አንዱ እውነተኛ አምላክ ነው /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት/፣ ይኸውም የእስራኤል የተለየነት፣ በጥቅም /ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ/
3. ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች፣ ሐ. "ኤሎሂም"

**138:2 "ወደ ቅዱስ መቅደስህ"** አይሁድና ሞስሊሞች ወደ ኢየሩሳሌም አቅንተው ነው የሚጸልዩት /ኋላ ላይ ሞስሊሞች ወደ መካ ቀየሩ/፡፡ ይህ ስፍራ ነው አንዱ እውነተኛ አምላክ ለማደር የመረጠው /ዘዳ. 12፡11/፣ በኪሩቤል ክንፎች መካከል፣ በኪዳን ታቦቱ ላይ /ዘጸ. 25፡22/ በቅድስተ ቅዱሳን፡፡ እሱም ሰማይና ምድር የተገናኙበት ስፍራ ነው፡፡

የዳዊት አገዛዝ ታሪካዊ መቼት ከሆነ፣ እንግዲያውስ "መቅደስ" መረዳት ያለበት እንደ "ታቦት" ቤት ነው፣ "በማደሪያው ድንኳን፡፡" እስራኤላውያን የሚጸልዩት

1. ከኢየሩሳሌም በራቁበት ጊዜ፣ ፊታቸውን ወደ ኢየሩሳሌም አዙረው /ዳን. 6፡10/
2. በመቅደስ በሚሆኑበት ጊዜ ፊታቸውን ወደ ታቦቱ አድርገው /መዝ. 28፡2/

▣ **"ስምህ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ /ብኪ/፡፡

▣ **"ቸርነት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቸርነት /ሄስድ/፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀቅ** | **"እውነት"** |
| **አየተመቅ፣ አእቅ፣** | |
| **ጄፒኤስኦኤ፣ የተእመቅ** | **"ታማኝነት"** |
| **አኢመቅ** | **"ቋሚነት"** |

የቃሉ (ቢዲቢ 54) ፍች በግሡ አጠቃቀም ሊታይ ይችላል (ቢዲቢ 52)፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ፡፡

▣ **"ቃልህ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ፡፡

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"እንደ ሁሉም"** |
| **አኪጀቅ** | **"ከሁሉም በላይ"** |

ይህ ሐረግ በዕብራይስጥ ግልጽ አይደለም፡፡ እሱም "በመላእክት ፊት" ከሚለው ጋር ይዛመዳል፣ የመዝ. 138፡1ለ፡፡ ደግሞም "የምድር ነገሥታት" ከሚለው ጋር ይዛመዳል፣ መዝ. 138፡4፡፡ ምንም ዓይነት የተለየ ነገር ይጥቀስ፣ በመዝሙረኛው ሐሳብ በጉልህ የሚያሳየው የእስራኤልን አምላክ አካል ነው፡፡ የእርሱ ባሕርይ ሉዓላዊ ነው /አኢመቅ/፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት /ብኪ/ እና ልዩ ርዕስ፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት /አኪ/፡፡

**138፡3** የያህዌ ምላሽ /ተተኳሪ/ ለመዝሙረኛው ጸሎት /ሁለት ያልተጠናቀቁ ግሦች/

1. ጉልህ አደረገው /"ግትር" ቢዲቢ 923/ ነገር ግን በዚህ ዐውደ-ጽሑፍ ላይ የሂፊል ያልተጠናቀቀ የተለየ አጠቃቀም "ጉልህ" ታሳቢ ፍቺ ነው

ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት /ገጽ 421/ ለኤምቲ (ቢ.ዲ.ቢ. 923፣ בהר ) "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል /መጠነኛ ጥርጣሬ/ እናም የየተመቅ፣ አየተመቅ ማሻሻያ ይጠቅሳል፣ "ማብዛት" ወይም "መጨመር" የሚለውን (ቢ.ዲ.ቢ. 915፣ הבר)፡፡

2. "በብዙ ኃይል" - ስሙ፣ ቢ.ዲ.ቢ. 738፣ የሚገልጸው ጥንካሬን ወይም ብርታትን ነው

እንዴት ዓይነቱን የንስሐ፣ የታመነ ጸሎት ያደርጋል፡፡ ጸሎት እኛና እግዚአብሔር ላይ ተጽዕኖ ያሳድራል /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የምልጃ ጸሎት/፡፡

▣ **"ነፍስ"** ሙሉ ማስታወሻ ተመልከት ኔፊሽ ላይ (ቢ.ዲ.ቢ. 659) ዘፍ. 35:18 በድረ-ገጽ መስመር www.freebiblecommentary.org.

## መዝሙር ፡ 138፡4-6

**[4]አቤቱ፥ የምድር ነገሥታት ሁሉ ያመሰግኑሃል**
**የአፍህን ቃል ሁሉ ሰምተዋልና።**
**[5]በእግዚአብሔርም መንገድ ይዘምራሉ**
**የእግዚአብሔር ክብር ታላቅ ነውና።**
**[6]እግዚአብሔር ከፍ ያለ ነውና፥**
**ወደ ችግረኞችም ይመለከታልና**
**ትዕቢተኞችንም ከሩቅ ያውቃል።**

**138:4-6** እንደ መዝ. 138:1-3 የሚገልጸው የመዝሙረኛውን ጸሎትና የያህዌን ምላሽ ነው፣ አሁን ይህ አንጓ የተመለከተው ለአሕዛብ ነው /ማለትም፣ "የምድር ነገሥታት ሁሉ"/፡፡

1. እነርሱ ምስጋና ያቀርባሉ – ቢ.ዲ.ቢ. 392፣ ኬ.ቢ. 389፣ *ሂፊል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. እነርሱ በእግዚአብሔር መንገድ ይዘምራሉ – ቢ.ዲ.ቢ. 1010፣ ኬ.ቢ. 1479፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

የፈሊጡ ምክንያት

1. የያህዌ መገለጥ /ማለትም፣ ቃላት/
2. የያህዌ መንገዶች /ማለትም፣ የተዋረዱትን ከፍ ያደርጋል፣ በትዕቢተኞች ላይ ይፈርዳል/፣ መዝ. 138፡6
3. የያህዌ ታላቅ ክብር /ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ክብር/

**138:4 "የምድር ነገሥታት ሁሉ"** ብኪ አሕዛብን በበርካታ ፊርጆች ይዘረዝራቸዋል፡፡

1. የያህዌ እና የመሲሑ ሀብት – መዝ. 2:8፤82:8፤ራዕ. 11:15
2. የእነርሱ ፍርሃት/ፍርድ – መዝ. 72:11፤102:15፤ኢሳ. 49:23
3. የእነርሱ አምልኮ – መዝ. 22:27፤66:4፤86:9፤138:4፤ኢሳ. 66:23፤ራዕ. 15:4፤ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ

**138:6 "እሱ ያውቃል"** ይህ ግሥ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለቀረበ ወዳጃዊ ግንኙነት ነው፡፡ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ፡፡

## መዝሙር ፡ 138፡7-8

**[7]በመከራ መካከል እንኳ ብሄድ፥ አንተ ሕያው ታደርገኛለህ**
**በጠላቶቼ ቍጣ ላይ እጆቼን ትዘረጋለህ፥**
**ቀኝህም ታድነኛለች።**
**[8]እግዚአብሔር ብድራትን ይመልስልኛል**
**አቤቱ፥ ምሕረትህ ለዘላለም ነው**
**አቤቱ፥ የእጅህን ሥራ ቸል አትበል።**

**138፡7-8** መዝሙረኛው ያለበትን ወቅታዊ ሁኔታ ይጠቅሳል፡፡

1. በመከራ መካከል ብሄድ፣ መዝ. 138:7 /ይህም መዝ. 138:3 ላይ ፍንጭ ተሰጥቶበታል/
2. አስፈሪ ጠላቶች አሉት፣ መዝ. 138:7ለ፤እነዚህ ጠላቶች እነማን ለመሆናቸው ርግጠኝነት የለም
   ሀ. እስራኤላውያን ሰዎች
   ለ. ጣዖት አምላኪ ጎረቤቶች
   ኤቢ /ገጽ 275-276/ የሚያስረግጡት ይህ መዝሙር እጅግ በተሻለ መተርጎም የሚኖርበት እንደ ንጉሣዊ መዝሙር ነው፣ በዳዊት አገዛዝ ጊዜ፣ ከዑጋሪቲካዊ ቅኔ ሥርወ-ቃላዊና ሰዋሰዋዊ መያያዝ ምክንያት፡፡
3. "እኔን የሚመለከተኝ/የሚገደኝ፣" መዝ. 138:8ሀ፡፡ ይህም ደግሞ ተለይቶ ያልተመለከተ ነው፣ ነገር ግን ዐውደ-ጽሑፉ የሚያመለክተው መንፈሳዊ ወይም ሃይማኖታዊ ሐሳብ መሆኑን ነው
4. "በሕይወት መቆየት" የሚለው ቃል አጠቃቀም /"በሕይወት አኑረኝ" ጠላቶችን ያመላክታል
   ሀ. እሱን ለመግደል ይሞክሩ ነበር
   ለ. ታምሞ ነበር

**138:7 "ቀኝህም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ፡፡

▣ **"አድነኝ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መዳን /ብኪ/፡፡

**138፡8ሀ** እንዴት ያለው ተስፋ ነው፣ ለታማኝ ተከታዮች ሁሉ፡፡

1. እኛ ሁላችንም መለኮታዊ ዓላማ አለን (መዝ. 57:2፤ፊሊ. 1:6)
2. የእምነታችን ባለቤት ዓላማውን በእኛ ውስጥ ያከናውናል/ይፈጽማል

**138፡8ለ "ምሕረት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት /ሄስድ/፡፡

▣ **"ለዘላለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም /ኦላም/፡፡

**138:8ሐ "አቤቱ፥ የእጅህን ሥራ ቸል አትበል።"** ግሥ (ቢዲቢ 951፣ ኬቢ 1276፣ ሂፊል ተጽዕኖዊ/ የሚገልጸው የያህዌን ታማኝነት ነው፣ ለዓላማው፡፡

"የእጆችህን ሥራ" የሚለው ሐረግ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ያህዌ የሰው ልጅን በመልኩና በአምሳሉ ለመፍጠሩ (ዘፍ. 1:26-27፤2:1-7)፡፡

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. "አማልክት" ማንን ነው የሚጠቅሰው፣ መዝ. 138፡1ለ ላይ ያለው?
2. "ምሕረት" እና "እውነት" የሚባሉትን የዕብራይስጥ ፍች ግለጽ፡፡ መዝ. 138፡2
3. የመዝሙር 138፡2 የመጨረሻ ስንኝ/መስመር ለመተርጎም ለምን እጅግ አስቸጋሪ ሆነ?
4. መዝ.138፡3 ለመተርጎም ለምን እጅግ አዳጋች ሆነ?
5. "የምድር ነገሥታት ሁሉ" የሚያመለክተው የፍርድ ትዕይንትን ነው ወይስ የአምልኮ ትዕይንትን?
6. "ችግር" ወይም "ጠላቶቼ" የሚሉትን መግለጽ ይቻላል፣ የመዝ. 138፡7?
7. መዝ. 138፡8 ምን ዓይነቱን ታላቅ እውነት ይገልጻል?

# መዝሙር 139
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የእግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ መገኘት እና ሁሉን አዋቂነት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ የዳዊት መዝሙር | እግዚአብሔር ሰውን ፍጹም ያውቀዋል | ጸሎት ከግል ጠላቶች ለመጠበቅ<br>(ሰቆቃ) | የእግዚአብሔር ፍጹም አዋቂነትና ክብካቤ | ምስጋና ለጌታ ሁሉን አዋቂነት |
| 139:1-6 | 139:1-6 | 139:1-6 | 139:1-6 | 139:1-3 |
| | | | | 139:4-6 |
| 139:7-12 | 139:7-12 | 139:7-12 | 139:7-12 | 139:7-8 |
| | | | | 139:9-10 |
| | | | | 139:11-12 |
| 139:13-16 | 139:13-16 | 139:13-18 | 139:13-18 | 139:13-14ለ |
| | | | | 139:14ሐ-15 |
| | | | | 139:16 |
| 139:17-18 | 139:17-18 | | | 139:17-18 |
| 139:19-22 | 139:19-22 | 139:19-24 | 139:19-22 | 139:19-20 |
| | | | | 139:21-22 |
| 139:23-24 | 139:23-24 | | 139:23-24 | 139:23-24 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የዕብራይስጥን ቅኔ ይጠቀማል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የዕብራይስጥ ቅኔ) ሥነ-መለኮታዊ የግሪክ ቃላትን ለመግለጽ፡ በሁሉም ስፍራ የሚገኝ፣ ሁሉን አዋቂ፣ እና ሁሉን ቻይ (አሸናፊ)። ያህዌ ፍጹም ዳኛ ነው።

ለ. ይህ መዝሙር የታማኝ ተከታይን ግላዊ እግዚአብሔርን ማወቅ ይገልጻል። እሱም ከእግዚአብሔር የቀድሞ ታሪካዊ ድርጊቶች ጋር አይያያዝም፣ ነገር ግን ከአሁን የእምነት ግንኙነት ጋር እንጂ።

ሐ. ጆን ካልቪን ብሏል፣ "እግዚአብሔርን ካላወቁ በቀር ራስን ማወቅ አይኖርም።" ይህ በዚህ መዝሙር ላይ ተግባራዊ የሆነ ይመስላል።

መ. ማሶረቲክ ዕብራይስጥ (ኤምቲ) ጽሑፍ እንደሚገልጸው የዚህ መዝሙር ደራሲ ዳዊት ነው። ታልሙድ (ሳንሄድሪን 38ለ) አስተዋጽዖውን የሚሰጠው ለአዳም ነው፣ ለመጀመሪያው። ሆኖም፣ ሴፕቱዋጂንት (LXX) ደራሲነቱን የሚሰጠው ለዘካርያስ ነው። የኤምቲ መግቢያዎች ሙት ባሕር ጥቅሎች ላይ አይገኙም። እኔ እንደ ተመስጧዊ አልቆጥራቸውም።

ሠ. አጭር የፍሬ - ሐሳብ ዝርዝር

1. እግዚአብሔር እኔን እንደሚያውቀኝ፣ መዝ. 139:1-6
2. እግዚአብሔር ከእኔ ጋር መሆኑ፣ መዝ. 139:7-12
3. የእግዚአብሔር የፈጠራ መጋቢነት፣ ለእኔ፣ መዝ. 139:13-16
4. የእግዚአብሔር ፍርድ ለእኔ፣ መዝ. 139:19-22
5. የታማኝ ተከታዮች ተገቢ ምላሽ፣ መዝ. 139:23-24

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡139፡1-6**

**[1]አቤቱ፥ መረመርኸኝ፥ አወቅኸኝም።**
**[2]አንተ መቀመጤንና መነሣቴን አወቅህ**
**አሳቤን ሁሉ ከሩቅ አስተዋልህ።**
**[3]ፍለጋዬንና ዕረፍቴን አንተ መረመርህ**
**መንገዶቼን ሁሉ ቀድመህ አወቅህ፥**
**[4]የዓመፃ ቃል በአንደበቴ እንደሌለ።**
**[5]አቤቱ፥ አንተ እነሆ የቀድሞውንና የኋላውን አወቅህ አንተ ፈጠርኸኝ፥**
**እጅህንም በላዬ አደረግህ።**
**[6]እውቀትህ ከእኔ ይልቅ ተደነቀች በረታች፥**
**ወደ እርስዋም ለመድረስ አልችልም።**

**139፡1 "ጌታ"** ይህ የእግዚአብሔር የኪዳን ስም ነው፣ ያህዌ፣ ከዕብራይስጥ "የመሆን" ግሥ፣ በአንድምታውም ዘላለም ኗሪውን፣ ብቸኛውን ሕያው አምላክ የሚያሳይ (ዘጸ. 3፡14)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ ***"መረመርኸኝ፥ አወቅኸኝም።"*** የመጀመሪያው ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 350፣ ኬቢ. 347፣ ቃል የተጠናቀቀ) መዝሙሩን ይጀምራል፣ ይፈጽማልም። መዝሙር 139፡21 ተተኳሪ ዓይነት ነው፣ ይኸውም መዝ. 139፡1 በአንድምታ በተተኳሪያዊ መልኩ እንዲረዳ የሚያደርግ። መሠረታዊው ሥርወ-ቃል "ወደ ውስጥ መቆፈር፣ ለማግኘት" የሚል ነው። እግዚአብሔር የሰዎችን ልብ ይመረምራል፣ (ኢዮብ 13:9፤1 ሳሙ. 16:7፤1 ነገ. 8:39፤1 ዜና. 28:9፤2 ዜና. 6:30፤መዝ. 7:9፤44:21፤ምሳ. 15:11፤20:27፤21:2፤ኤር. 11:20፤17:9-10፤20:12፤ሉቃስ 16:15፤ሐዋ. 1:24፤15:8፤ሮሜ. 8:27)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር ሕዝቡን ይፈትናል።

▣ **"አወቅኸኝም።"** የብኪ ቃል "ማወቅ" እዚህጋ ጥቅም ላይ የዋለው "ቅርብ ባልንጀራነትን፣ ግላዊ እውቀትን" ለማሳየት ነው፣ (ዘፍ. 4፡1፤ ኤር. 1፡ 5፤ ይህ ያልተጠናቀቀ ጥቅም ላይ የዋለው በተጽዕኗዊ መልኩ ነው፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ)።

**139፡2 *"መቀመጤንና መነሣቴን"*** የእግዚአብሔር ፍጹም እውቀት፣ የእያንዳንዱን ግለሰብ ሕይወት (ማለትም፣ ዘዳ. 6፡7) መዝ. 139፡2-4 ላይ ተገልጿል።

1. *መቀመጥ — መነሣት*፣ መዝ. 139፡2
2. *መጓዝ — ማረፍ*፣ መዝ. 139፡3
3. ከቃል በፊት — አንተ ታውቀዋለህ፣ መዝ. 139፡4
4. መዝ. 139፡2ለ፤3ለ፣ እና 4ለ እንደ ማጠቃለያ ዓረፍተ-ነገሮች ያገለግላሉ

▣ "ሐሳብ" የሚለው ቃል የተተረጎመው (ቢ.ዲ.ቢ. 946 III) እዚህጋ ብቻ እና መዝ. 139፡17 ላይ ነው የሚገኘው። ቢ.ዲ.ቢ. የእርሱ ፍች ያለው "ዓላማ" ወይም "ግብ" በሚል ነው። LXX እሱን የሚተረጉመው በተመሳሳይ ሥር፣ "ባልንጀሮች" በሚል ነው (ዲ.ቢ. 846) መዝ. 139፡17 ላይ፣ ነገር ግን "ሐሳቦች" የሚል አለው፣ 139፡2 ላይ።

**139፡3 "ፍለጋዬን አንተ መረመርህ"** "መመርመር" የሚለው ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 279፣ ኬቢ. 280፣ ፒል የተጠናቀቀ) የተለመደ ፍችው "መበተን" ነው፣ እዚህ ግን፣ እዚህጋ ብቻ፣ የሚገልጸው መውቃትን ወይም ማበራየትን ነው። ኬቢ. ሥሩን የሚመለከተው "መለካት" በሚል ፍች ነው (ኬቢ. 280 II) "ማወቅ" በሚለው መልኩ።

"መንገድ" የሚለው ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 73) ለአንዱ ሕይወት ዘይቤ ነው (ኢዮብ 14:16፤31:4)። ጽንሰ-ሐሳቡም ከ "ዘላለም መንገድ" ጋር ትይዩ ነው፣ ከመዝ. 139:24።

▣ ***"ዕረፍቴን"*** ሴፕቱዋጂንት "መኝታ" የሚል ቃል አለው። ይህም ሊሆን የሚችለው አንድም የሌሊት መቆያ ስፍራዎች፣ አንዱ የሚተኛበት፣ በጉዞ ላይ እንዳለ፣ ወይም የአንዱ የግብረ-ሥጋ ድርጊት ነው (ማለትም፣ እግዚአብሔር የሰዎችን ድርጊቶች ሁሉ ያውቃል)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"በቅርበት ያውቃል"** |
| **አኪጀቅ፣ አየተመቅ** | **"አወቅህ"** |
| **አእቅ** | **"አወቅህ"** |
| **አኢመቅ** | **"እያንዳንዱን ዝርዝር"** |
| **ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ** | **"የሚታወቅ"** |

የዕብራይስጡ ሥር (ቢዲቢ 698) በርካታ ፍችዎች አሉት።

1. 698 I – *ቃል*፣ "ግልጋሎት ሰጭ" ወይም "ጠቀሜታ"
   – *ሂፊል* እዚህጋ ጥቅም ላይ ውሏል እና ዘኍ. 22:30፤ኢዮብ 22:21 ላይ፣ "በቅርበት ማወቅ"
2. 698 II – "አደጋ ማስከተል፣" መክ. 10:9 (*ኒፋል*)
3. 698 III – "ደሀ መሆን፣" ኢሳ. 40:20 (*ፖል*)

እነርሱ ሁሉ ተመሳሳይ ተናባቢ ሥር እና ማሶረቲካዊ አናባቢ ነጥቦች አሏቸው። ዐውደ-ጽሑፍ ብቻ ነው ለፍችው ፍንጭ ሊሰጥ የሚችል።

**139:4 "በአንደበቴ ቃል ከመኖሩ በፊት እንኳ"** ፔሺታ "ማሳት" የሚል ሲኖረው፣ ሴፕቱዋጂንት ደግሞ "የዓመጻ ቃል" የሚል ሐረግ አለው። የጥንቶቹ ቅጅዎች የሚያምኑት መዝ. 139:4 ከሰው ልጅ የከፋት ጎን ጋር የሚዛመድ መሆኑ ግልጽ ነው። የሰዎች የንግግር ቃል ማን መሆናችንን በርግጠኝነት ይገልጻል (ማቴ. 12:36፣37፤ማርቆስ 7:15)።

**139:5 "አንተ ከበብከኝ"** ሴፕቱዋጂንትና ፔሺታ "ፈጠርከኝ" የሚል ግሥ አላቸው፣ በ "ከበብከኝ" ምትክ (ቢዲቢ 848፣ ኬቢ 1015፣ *ቃል* የተጠናቀቀ)። ሆኖም፣ ከሚከተለው ሐረግ የተነሣ፣ "መከበብ" እጅግ የተሻለ ተገቢ ይመስላል። ይህ የዕብራይስጥ ሥር (ቢዲቢ 848 II) ወታደራዊ ፍች አለው (ኢሳ. 29:3) ወይም የመታገት ስሜት መኃልየ መኃልይ 8:9)። እዚህ የሚያመለክተው የያህዌን ሉዓላዊ ተቆጣጣሪነትና መሪነት ነው፣ የሰውን ሕይወት።

የዕብራይስጥ ቃላት "በኋላ" እና "በፊት" የሚያንጸባርቁት የዕብራይስጥ ቃላትን "ምስራቅ" እና "ምዕራብ" ነው (ኢዮብ 18:20)።

▣ **"እጅህንም በላዬ አደረግህ።"** ይህ ሰዋዊ ዘይቤ ቋንቋ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሲገለጽ)። "እጅ" የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ የኃይልና የተቆጣጣሪነት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እጅ)።

*መዝሙር 139:5ለ የያህዌን ሉዓላዊነትና ተቆጣጣሪነት የሚያሳይ መግለጫ ነው፣ የሰብዓዊ ፍጡሩን (መዝ. 139:10)። ይህ እውቀት ታማኝ ተከታዮቹን ሲያበረታታ፣ የማይታዘዙትን ያስፈራል።*

**139:6 "እውቀትህ ከእኔ ይልቅ ተደነቀች በረታች፥"** ሴፕቱዋጂንት መዝ. 139:6ን የሚያስቀምጠው ከቀጣዩ አንቀጽ ጋር ነው። ይህ ሐረግ የእግዚአብሔርን እውቀት ያንጸባርቃል፣ ይኸውም ለሰው ልጅ ለመረዳት እጅግ የሚከብድ (መዝ. 139:14፣17፣18፤መዝ. 40:5፤ኢሳ. 55:8፣9፤ሮሜ. 11:33)። ባጠቃላይ እግዚአብሔርን ማመን ይገባናል፣ ሙሉ ለሙሉ ሳንረዳው (ማለትም፣ ኢዮብ 1-2፣42)።

የዕብራይስጡ ቃል "አስደናቂ" ፍችው ሊሆን የሚችለው "አስቸጋሪ" ነው (ዘዳ. 30:11 እና ምሳ. 30:18፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተአምራት)።

> ***መዝሙር :139:7-12***
>
> **[7]ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ?**
> **ከፊትህስ ወዴት እሸሻለሁ?**
> **[8]ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ አለህ።**
> **ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ።**
> **[9]እንደ ንስር የንጋትን ክንፍ ብወስድ፥**
> **እስከ ባሕር መጨረሻም ብበርር፥**
> **[10]በዚያ እጅህ ትመራኛለች፥**
> **ቀኝህም ትይዘኛለች።**
> **[11]በውኑ ጨለማ ትሸፍነኛለች ብል፥**
> **ሌሊት በዙሪያዬ ብርሃን ትሆናለች**
> **[12]ጨለማ በአንተ ዘንድ አይጨልምምና፥**
> **ሌሊትም እንደ ቀን ታበራለችና**
> **እንደ ጨለማዋ እንዲሁ ብርሃንዋ ነው።**

**139:7 "ከመንፈስህ ወዴት እሄዳለሁ?"** ይህንን ጥያቄ በትክክል በምን መልኩ እንደሆነ ለመረዳት ርግጠኝነት የለም። አንዳንዶች የሚመለከቱት የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር ለመሸሽ ሲሞክር እንደ ሆነ ነው፣ ክፉ በመሆኑ ምክንያት። ሌሎች የሚመለከቱት እንደ ንግግር ብልሃት ነው፣ የእግዚአብሔርን በሁሉ ስፍራ መሆን ለማሳየት። ግልጽ የሆነው ነገር "መንፈስህ" በዚህ ቁጥር ላይ "ከፊትህ" ከሚለው ከቀጣዩ መስመር ጋር ትይዩ መሆኑ ነው። ይህ የተሟላው የአኪ ሥላሴአዊ አይደለም (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሥላሴ) "መንፈስ" የሚለው ቃል አጠቃቀም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ንቁ መገኘት መግለጫ መንገድ ነው (ዘፍ. 1:2)። እኔ ይሄንን ጽንሰ-ሐሳብ ብጽፈው ሊሆን የሚችለው፣ "ከእግዚአብሔር መደበቂያ ስፍራ የለም" የሚል ነው (ኤር. 23:23፣24)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመንፈስ አካላዊነት።

**139:8 "ወደ ሰማይ ብወጣ፥ አንተ በዚያ አለህ።"** ይህ በጥሬው "ሚዛን" ማለት ነው (ቢዲቢ 701፣ ኬቢ 758፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ)። ይህም ከመዝ. 103:11 ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው፣ የእግዚአብሔርን በሁሉም ስፍራ መገኘት፣ ሰማይ ከላይ ሲኦል ከታች ሩቅ እንደሆነ።

በቀጣዮቹ ጥቂት ቁጥሮች "ተቃርኖዎች" እንዴት ጥቅም ላይ እንደዋሉ ተመልከት፣ የእግዚአብሔርን እውነት ሙሉ ዳርቻ ለማሳየት፣ ስለ እግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነትና በሁሉም ስፍራ መገኘት።

1. ወደ ሰማይ ብወጣ — መኝታዬን ሲኦል ባደርግ፣ መዝ. 139:8
2. የንጋት ክንፎች (ማለትም፣ ምስራቅ) — የባሕሩ ሩቅ ክፍል (ማለትም፣ የሜዲትራኒያን ባሕር ወደ ምዕራብ)፣ መዝ. 139:9
3. ጨለማ — ብርሃን፣ መዝ. 139:12

እግዚአብሔር በሁሉም ስፍራ አለ። ማንም ከእርሱ መሸሽ አይችልም!

▣ **"ወደ ሲኦልም ብወርድ፥ በዚያ አለህ።"** ብኪ ላይ ብዙ ምንባቦች አሉ፣ እግዚአብሔር በሙታን ግዛት እንደሚገኝ የሚናገሩ (ኢዮብ 26:6፤ መዝ. 15:11፤አሞጽ 9:2)። "ሲኦል" የሚለው ቃል "ሃደስ" ከሚለው የአኪ ቃል ጋር ተመሳሳይ ነው፣ እናም መተርጎም የሚኖርበት "የሙታን ግዛት" ወይም "የታችኛው ዓለም" በሚል ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሙታን የት ናቸው?

**139፡9 "ብወስድ... ብበርር"** መላ ምታዊው አንቀጽ (ቢዲቢ 49) መዝ. 139፡8ሀ ላይ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ነገር ግን በተመሳሳይ 8ለ፣ 9ሀ፣ 9ለ፣ 11ሀ ላይ።

"እንኳ" የሚለው ተውሳከ ግሥ (ቢዲቢ 168) በተመሳሳይ መንገድ ነው ጥቅም ላይ የዋለው፣ መዝ. 139፡10ሀ፣ 12ሀ ላይ።

መዝሙር 139፡8-12 ለሁለቱ የ139፡7 ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣል። እሱ መላምታዊ ቋንቋ ነው፣ ነጥቡን ለማበጀት ጥቅም ላይ የዋለ።

▣ **"እስከ ባሕር መጨረሻም"** ይህ ሐረግ በጥሬው "ከፀሐይ መውጫ እስከ መግቢያ፣" ማለት ነው፣ እሱም ከመዝ. 130፡12 ጋር ተመሳሳይ የሆነ።

**139፡10 "በዚያ እጅህ ትመራኛለች፥**
**ቀኝህም ትይዘኛለች።"** ልማዳዊው ትርጉም ይሄንን ቁጥር የሚወስደው የእግዚአብሔርን ግላዊ ምሪትና ጥበቃ ለመግለጽ ነው። ሆኖም፣ የዕብራይስጡ መዝ. 139፡10 እና 11 የሚለው የጨለማ ሰውኛ ዘይቤ ወይም የግል ጠላት የእግዚአብሔርን ሰው እያባረረው መሆኑን ነው።

**139፡11 "በውኑ ጨለማ ትሸፍነኛለች ብል፥"** "ጨለማ፣" መዝ. 139፡11፤ "ሌሊት፣" መዝ. 139፡11፤ "ጨለማ፣" መዝ. 139፡12፤ "ሌሊት፣" መዝ. 139፡12 የሚሉት ቃላት ሲኦልን የሚያመለክቱ ይመስላል (መዝ. 139፡15)። የጥንቶቹ የአይሁድ ትርጉሞች በራሺ እና ኢብን ዕዝራ፣ ከአዓት ጋር፣ መዝ. 139፡11ን የሚያስቡት የማምለጥ ሙከራ አድርገው ነው፣ (1) ኃጢአተኛ ሰው በጨለማ ውስጥ ወይም (2) ታማኝ ከኃጢአተኛ አሳዳጆች።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | ***"መያዝ"*** |
| **አኪጀቅ** | ***"መውደቅ"*** |
| **አየተመቅ፣ አኢመቅ፣ ቫልጌት** | ***"መሸፈን"*** |
| **አእቅ** | ***"መደበቅ"*** |
| **ጀፒኤስአኤ** | ***"መደበቅ"*** |
| **የተእመቅ** | ***"መሸሸግ"*** |

ኤምቲ ךו – አለው (ቢዲቢ 1003)፣ ፍችውም "መጉዳት" (ዘፍ. 3:15፤ኢዮብ 9:17) ነገር ግን ይህ ከዐውደ-ጽሑፉ ጋር የሚገጥም አይመስልም። ስለዚህ፣ አንዳንድ ሊቃውንት ማሻሻያ ያደርጋሉ ለ ייְנכּישׁ (ቢዲቢ 962) "ማገጃ" ወይም "አጥር" (ማለትም፣ ለመከለል ወይም ለመሸፈን)።

"ጨለማ" ምንም ማለት ይሁን፣ እግዚአብሔር ይቆጣጠረዋል፣ እናም የእርሱ ታማኝ ተከታዮች ሊፈሩት አይገባም! እሱ እንዲያውም ለራዕይ ዕድል የሚሰጥ ይሆናል (ዘፍ. 15፡12) ወይም ለመታደግ (የግብፅ መቅሠፍት፣ ዘጸ. 10፡19-21፤ መዝ. 105፡28)።

**139፡12 "ጨለማ በአንተ ዘንድ አይጨልምምና፥"** ጨለማ ሊሆን የሚችለው (1) የብርሃን ተቃራኒ፤ (2) የብርሃን ጠላት፤ (3) የአንዱ ግላዊ ጠላት፤ ወይም (4) የሌሊት ጊዜ።

ጨለማ የጥንቶቹን ያስደነግጥ ነበር። እነርሱም ዘወትር ሰውኛ ዘይቤ ያደርጉት ነበር፣ በሰማይ ያለ ድምጹንና ብርሃኑን፣ እንደ አማልክት ወይም ምልክቶች። እግዚአብሔር ጨለማን ይቆጣጠራል!

▣ **"ጨለማና ብርሃን በፊትህ ተመሳሳይ ናቸው"** ምንም ዓይነት መሮጫ ወይም መደበቂያ ስፍራ የለም፣ ከፈጣሪ (መዝ. 139፡7)!

***መዝሙር ፡139፡13-16***

**13አቤቱ፥ አንተ ኵላሊቴን ፈጥረሃልና፥**
**በእናቴም ሆድ ሰውረኸኛል።**
**14ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ**
***ሥራህ ድንቅ ነው፥***
**ነፍሴም እጅግ ታውቀዋለች።**
**15እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፥**
**አካሌም በምድር ታች በተሠራ ጊዜ**
**አጥንቶቼ ከአንተ አልተሰወሩም።**
**16ያልተሠራ አካሌን ዓይኖችህ አዩኝ**
**የተፈጠሩ ቀኖቼ ሁሉ**
**አንድ ስንኳ ሳይኖር**
**በመጽሐፍህ ተጻፉ።**

**139፡13**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣ አየተመቅ** | ***"ተበጀ"*** |
| **አእቅ፣ አኢመቅ፣ ጀፒኤስአኤ** | ***"ተፈጠረ"*** |

**የተእመቅ** **"ተበጀ"**
**LXX** **"ተያዘ"**

ግሥ (ቢዲቢ 888፣ ኬቢ 1111፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) የተለመደ ፍችው "መግዛት" ነው፣ ነገር ግን እሱ ለእግዚአብሔር የፈጠራ ድርጊቶች ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ ውሏል (ዘፍ. 14:19፤22፤ዘዳ. 32:6፤ምሳ. 8:22)። እዚህጋ የሚገልጸው የእግዚአብሔርን የተለየ፣ ግላዊ ክብካቤ ነው፣ ሰውን ሲፈጥር። አዳምን (ዘፍ. 2:8) እና ሔዋንን (ዘፍ. 2:18፤21-22) በልዩ ክብካቤና ዓላማ እንደፈጠረ፣ እንዲሁ ደግሞ እያንዳንዱን ሰው፣ በመልኩና በአምሳሉ የተፈጠረውን (ዘፍ. 1:26-27)። ሰዎች የተለዩ ናቸው!

▣ **"ውስጣዊ አካል"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል (ቢዲቢ 480) የሚገልጸው ታችኛውን የሰው ውስጣዊ አካል ነው (በተለይም፣ "ኩላሊት")፣ ይኸውም የዕብራይስጥ ፈሊጥ፣ ለሰው ስሜቶችና ፍቃድ። ይህ የእግዚአብሔር ፍጥረት አንድምታው ቅድመ-ወሊድ ብጅት ነው (ኤር. 1፡5) የሰው እና የስብዕናው።

▣ **"በእናቴም ሆድ ሰውረኸኛል።"** "መሸመን" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 697 II፣ ኬቢ 754 II) በጥሬው ያልተለመደ የዕብራይስጥ ቃል ነው "የእጅ ሥራ ማበጀት።" እሱም በጥቂት ስፍራ ብቻ ነው የሚገኘው።

1. *ቃል* – መዝ. 139:13
2. *ኒፋል* – ምሳ. 8:23 (ተመሳሳይ ቃል ሊሆን ይችላል)
3. *ፖል* – ኢዮብ 10:11

ተመሳሳይ ቃል (ኬቢ 754 III) "መሸፈን" በሚል ተተርጉሟል (ሰቆ. 3:43፤44)። ቃሉ ያልተዘወተረና አሻሚ ነው ነገር ግን ከዐውደ-ጽሑፉ አኳያ ፍችው ግልጽ ነው። የዕብራይስጥ ትይዩ እጅግ የሚረዳ ነው፣ እነዚህን ያልተለመዱ ቃላት ለመተርጎም።

**139፡14-16** ዩቢኤስ *ማስታወሻ መጽሐፍ* (ገጽ 1130) የሚለው "የቁጥር 14-16 ትርጉም በአስቸጋሪዎች የተሞላ ነው፣ እናም እጅግ ጥቂት አታቾች (ኮሜንታተርስ) ወይም ተርጓሚዎች ናቸው ስለ ማሶረቲክ ጽሑፍ ትክክለኛ ፍች ቀኖናዊ የሚሆኑት።" ይህ እንዲህ በመሆኑ ምክንያት፣ ምንም ዓይነት ዶክትሪን በሌሎች የቅዱስ ቃሉ ክፍሎች በግልጽ ትምህርቱ ያልቀረበ በእነዚህ ቁጥሮች ላይ መመሥረት አይኖርበትም። የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ቅኔ አስቸጋሪ (አምታች) ዓይነት ነው። እሱ ለስሜታዊ አንድምታ ነው፣ እናም ለሰዋሰዋዊ እና ሥርወ-ቃላዊ ትንታኔዎች አስተዋጽዖ አይኖረውም። ዐውደ-ጽሑፍ፣ ዐውደ-ጽሑፍ፣ ዐውደ-ጽሑፍ ዋነኛ ነገር እንደሆነ አስታውሱ። የዕብራይስጥ ትይዩነት ደግሞ የተሻለ መመሪያ ነው፣ ከተመሳሳይ ሴማዊ ሥር ቋንቋ ይልቅ! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የዕብራይስጥ ቅኔ።

**139፡14 "ግሩምና ድንቅ ሆኜ ተፈጥሬአለሁና አመሰግንሃለሁ"** ሴፕቱዋጂንትና የተመቅ ሰውን ሳይሆን እግዚአብሔርን ነው የዓረፍተ-ነገሩ ባለቤት የሚያደርጉት። አዲሱ እንግሊዝኛ ቅጅ፣ የሙት ባሕር ጥቅሎችን ተከትሎ፣ ከዚህ መረዳት ጋር የተስማማ ይመስላል። ኤምቲ "እኔ" የሚል አለው።

ሁለቱ ቃላት

1. በግሩም ሁኔታ – ቢዲቢ 431፣ ኬቢ 432፣ *ኒፋል* አንቀጽ
2. በድንቅ ሁኔታ – ቢዲቢ 811፣ ኬቢ 930፣ *ኒፓህል* የተጠናቀቀ

እነዚህ ሁለት ቃላት እግዚአብሔርን የሚያመለክቱ ከሆነ፣ እንግዲያውስ እነርሱ ከቀጣዩ የቅኔ ስንኝ (መስመር) ጋር ትይዩ ናቸው፣ "ሥራህ ድንቅ ነው" (መዝ. 139:14ለ)።

ጀፒኤስኦኤ ይህንን አንጓ የሚተረጉመው (መዝ. 139፡13-16) እግዚአብሔር ሰውን እንደፈጠረው ለማመልከት ነው፣ የእግዚአብሔር ገለጻ ሳይሆን፣ መዝ. 139፡14 ላይ።

**139:15**
**አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣**
**አየተመቅ፣ ጀፒኤስኦኤ** **"ማዋቀሪያ"**
**አእቅ** **"አጥንቶች"**
**የተእመቅ** **"አካል"**

የዕብራይስጡ ስም (ቢዲቢ 787፣ ኬቢ 870) ዘወትር ፍችው "ብርታት" ነው (ዘዳ. 8:17)። እዚህጋ ብቻ ቢዲቢ "አጥንቶች" የሚል አለው (ኒዶቲ ተመልከት፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 499-500)፣ ምንም እንኳ ሥሩ ለመሥዋዕት አጥንቶች ጥቅም ላይ ቢውልም (ዘኍ. 9:12) ወይም ለሰው አጥንቶች (ዘኍ. 19:16፤18)። እዚህጋ ስሜቱ የሰው አጽም ነው።

▣ **"እኔ በስውር በተሠራሁ ጊዜ፥"** ይሄንን ቁጥር በበርካታ መንገዶች መረዳት ይቻላል፡

1. "ምሥጢር" ከሚለው ቃል ጋር በተያያዘ (ቢዲቢ 712) እና ትይዩው ሐረግ፣ "በምድር በታች" ለሲኦል ሌላው ስም ነው (መዝ. 63:9፤ ኢዮብ 14:13፤40:13፤ኢሳ. 45:19)
2. ይህን ከአዳም አፈጣጠር ጋር በማያያዝ፣ ከአፈር (ዘፍ. 2፡7) እና የእኛም ከአፈር መፈጠር፣ ከምድር በታች ለሚለው ሰውኛ ዘይቤ ሆኗል (መክብብ 40፡1)
3. ሌለኛው ታሳቢ ሊሆን የሚችለው የማኅፀንን "ድብቅነት" እና የታችኛውን ዓለም "ድብቅነት" በቅኔአዊ ምናባዊነት መጠቀም ነው፣ ሥነ-መለኮታዊ ማስረገጫ ሳይሆን

▣
**አአመመቅ፣ አኪጀቅ** **"በጥበብ የተበጀ"**
**አየተመቅ** **"በጥበብ የተሠራ"**
**አእቅ** **"አንድ ላይ"**
**አኢመቅ** **"የተበጀ"**
**ጀፒኤስኦኤ** **"የተበጀ"**
**የተእመቅ** **"የተሠራ"**

የዕብራይስጡ *ሥር*፣ רקם (ቢዲቢ 955)፣ ፍችው “ኅብረ-ቀለም” ነው። *ሖል* እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው። አየተመቅበጥሬው ነው። *ሥሩ* ግን ሊያመለክት የሚችለው “ማቡካት”ን ነው፣ ሸክላ ወይም ሊጥ (ኤቢ ገጽ 294፤አእቅ፣ አኢመቅ፣ ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ)።

**139፡16 “ዓይኖችህ”** ብኪ ዘወትር ሰዋዊ ዘይቤ ቋንቋን ይጠቀማል፣ እግዚአብሔርን ለመግለጽ። ሰዎች ሌላ መጠቀሚያ ቋንቋ የላቸውም፣ ነገር ግን ዘወትር ምስያ ብቻ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እግዚአብሔር እንደ ሰው ሲገለጽ።

▣ **“ያልተሠራ አካሌን”** ይህ ለልዩ ፍች ጥቅም ላይ የሚውል ቃል ደግሞ በሁለት መንገዶች መረዳት አግኝቷል፡

1. የፅንስ እድገት፣ እሱም በእግዚአብሔር የሚታወቅ (መዝ. 139:13-16ሀ፤ ኤቪ፣ አርቪ፣ አእቅ፣ ጀፒኤስአኤ
2. ሕይወት ሁሉ በእግዚአብሔር ስለመታወቁ፣ ከልደት በፊት እንኳ (LXX፣ የተእቅ፣ ኢመቅ፣ አአመቅ፣ አእቅ)፣ በመዝ. 139:16ለ ዐውደ-ጽሑፋዊ መያያዝ ላይ በመመሥረት

“ያልተሠራ” (ቢዲቢ 166) “መጠቅለል” ከሚለው *ሥር* ነው (2 ነገ. 2:8) ነገር ግን እዚህጋ በአራማዊ መልኩ “ያልተጠናቀቀ ዕቃ” ነው። ኤቢ (ገጽ 295) እሱን የሚተረጉመው እንደ “ሕይወት ደረጃዎች” ነው፣ ከዑጋሪቲክ *ሥር*።

▣

**አአመመቅ** **“የተበጀ”**
**አኪጀቅ፣ የተእመቅ** **“የተሠራ”**
**አየተመቅ፣ ጀፒኤስአኤ** **“የተበጀ”**
**አእቅ** **“የተሰጠ”**
**አኢመቅ** **“የተጻፈ”**

*ግሡ* (ቢዲቢ 427፣ ኬቢ 428፤አውንስ፣ *የብኪ ትንታኔ ቁልፍ፡ ፖል* የተጠናቀቀ ብሎ ሲጠራው፣ የብኪ *ትንታኔ መመሪያ ቃል* ተገብሮ በማለት ይጠራዋል) የሸክላ ሠሪን ፈጠራ ይገልጻል (ኤር. 1፡5)። ይህ *ግሥ*፣ በዚህ መዝሙር ላይ እንደሚገኙ እንደ ሌሎች በርካቶች፣ የእግዚአብሔርን ሉዓላዊ ድርጊቶችና ፍቃድ ይገልጻል።

▣ **“ሁሉም በመጽሐፍህ ተጻፉ።”** ይህ የሚገልጸው ሁለቱን መጻሕፍት ነው፣ ዳን. 7፡10 እና ራዕ. 20፡12 ላይ የተጠቀሱትን፡ (1) የሕይወት መጽሐፍ (ዘጸ. 32:32፤መዝ. 69:25፤ሉቃስ 10:20) ወይም (2) የመታሰቢያ መጽሐፍ (መዝ. 56:8፤ሚል. 3:16)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሁለቱ መጻሕፍት።

እግዚአብሔር ሕይወታችንን፣ ሐሳባችንን፣ እና ድርጊታችንን ያውቃል፣ በጊዜው ከመሆናቸው በፊት (ራዕ. 13፡8)።

## መዝሙር ፡139፡17-18

**17አቤቱ፥ አሳቦችህ በእኔ ዘንድ እንደ ምን እጅግ የተከበሩ ናቸው!**
**ቍጥራቸውም እንደ ምን በዛ!**
**18ብቈጥራቸው ከአሸዋ ይልቅ ይበዛሉ**
**ተነሣሁም፥ እኔም ገና ከአንተ ጋር ነኝ።**

**139፡17 “አቤቱ፥ አሳቦችህ በእኔ ዘንድ እንደ ምን እጅግ የተከበሩ ናቸው!”** “የተከበሩ” የሚለው ፍች ከዕብራይስጥ *ሥር* “ከባድ” ወይም “ከባዳ” ነው (ቢዲቢ 429፣ መዝ. 116:15)። ሴፕቱዋጀንት ይሄንን ሐረግ የሚተረጉመው፣ “ወዳጆችህ፣ ጌታ ሆይ፣ በእኔ እጅግ ከበሩ” በሚል ነው። ለመዝ. 139፡17 ትይዩ መዝ. 40፡5 ተመልከት።

▣ **“ቍጥራቸውም እንደ ምን በዛ!”** በርካታ ትርጓሜያዊ ጉዳዮች አሉ፣ እዚህ ሐረግ ላይ።

1. “ብዙ” የሚለው ቃል (ቢዲቢ 782 II) “አጥንቶች” በሚል ነው የተተረጎመው፣ መዝ. 139፡16 ላይ፣ ነገር ግን በመካከላቸው ምንም ዓይነት ዐውደ-ጽሑፋዊ ግንኙነት ያለ አይመስልም።
2. “ቁጥር” የሚለው ቃል (ቢዲቢ 910 I) በጥሬው “ራስ” ነው። እሱም “የቁጥሮች ድርድር ድምር” ሊሆን ይችላል። የጥንቶቹ ወደ ላይ ነው የሚደምሩት፣ ወደ ታች ሳይሆን። ይህም የተሻለ ትይዩ ይፈጥራል፣ ለመዝ. 139፡16ሀ።
   ሆኖም፣ ኤቢ (ገጽ 296) የሚያስረግጠው የተሻለ ትርጉም “ዋነኛ ነገር” ነው፣ መዝ. 119፡160ን ተከትሎ።
   LXX ይሄንን ቃል የሚተረጉመው “ገዥዎች” ወይም “አለቆች” በሚል ነው። ግልጽ የሆነ አሻሚነት እዚህጋ አለ። ይህ የዕብራይስጥ ቅኔ መሆኑን አስታውስ፣ በርካታ ልዩ ትርጉም ያላቸውን ቃላት እና ያልተዘወተሩ ቃላትን የሚጠቀም።

**139፡18 “ብቈጥራቸው ከአሸዋ ይልቅ ይበዛሉ”** መዝሙር 139፡17 እና 18 አስደናቂ ነው፣ ማለትም፣ ሁሉን የሚያውቀው፣ በሁሉ ብርቱ የሆነው፣ ሁልጊዜም የሚገኘው አምላክ ለእያንዳንዱ ሰብዓዊ ፍጡሩ ክብካቤ ማድረጉ!

▣ **“ተነሣሁም፥ እኔም ገና ከአንተ ጋር ነኝ።”** “መንቃት” የሚለው ሐረግ በዕብራይስጥ የተጠናቀቀ የግሥ ጊዜ ነው። ስለ ፍችው በርካታ ንድፈ-ሐሳቦች አሉ።

1. ማለትም፣ እሱ የሚያመለክተው የዕብራይስጥ ጽንሰ-ሐሳብ የእግዚአብሔርን መገኘት ነው (መዝ. 73፡23)
2. ማለትም፣ አንዳንድ የዕብራይስጥ ጽሑፎች “የተጠናቀቀ” የሚል ቃል አላቸው፣ “ባርኮቶችህን ቆጥሮ ለማጠናቀቅ” በሚል መልኩ
3. አንዳንዶች ይሄንን የሚወስዱት ከእግዚአብሔር ጋር እንደሆነ የዘላለም ሕይወት ነው (መዝ. 17:15፤23:6)
4. መዝሙረኛው እንቅልፍ ወሰደው የእግዚአብሔርን ባርኮቶች ሲቆጥር እናም እንደ ገና ሲነቃ አሁንም እዚያ አገኘው (ምክንያቱም ቆጠራውን ማጠናቀቅ ስላልቻለ፣ መዝ. 3:5፤ምሳ. 3:24)።

**መዝሙር ፡139፡19-22**

[19]አቤቱ፥ አንተ ኃጢአተኞችን የምትገድል ከሆንህስ፥
የደም ሰዎች ሆይ፥ ከእኔ ፈቀቅ በሉ።
[20]በክፋት ይናገሩብሃልና
ጠላቶችህም በከንቱ ያምፁብሃል።
[21]አቤቱ፥ የሚጠሉህን እኔ የጠላሁ አይደለሁምን?
ስለ ጠላቶችህም አልተሰቀቅሁምን?
[22]ፍጹም ጥል ጠላኋቸው፥
ጠላቶችም ሆኑኝ።

**139፡ "አቤቱ፥ አንተ ኃጢአተኞችን የምትገድል ከሆንህስ፥"** በመጀመሪያ ይህ የመጨረሻ አንጓ በዐውደ-ጽሑፉ አላግባብ የገባ ይመስላል፣ ነገር ግን በርግጥ የጻድቁ አምላክ ሐሳብ እና በዚህ ኃጢአተኛ ዓለም የእርሱን አካላዊ መገኘት ቀጣይነትን የሚያሳይ ነው። ኃጢአተኞች በአምስት ሐረጎች ባሕርያቸው ተገልጿል።

1. እነርሱ ነፍሰ-ገዳዮች ናቸው፣ መዝ. 139፡19ለ
2. እነርሱ በክፋት ነው የሚናገሩት፣ መዝ. 139፡20ሀ
3. እነርሱ የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ ይጠራሉ፣ መዝ. 139፡20ለ
4. እነርሱ እግዚአብሔርን ይጠላሉ፣ መዝ. 139፡21ሀ
5. እነርሱ በእግዚአብሔር ላይ ይነሣሉ፣ መዝ. 139፡21ለ

መዝሙረኛው የሚመኘው የሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30 ርግማን እንዲሰርስባቸው ነው። "ሁለቱ መንገዶች" ግልጽ የሆነ ውጤት አላቸው በሰዓትና በዘላለማዊነት ላይ (ዘዳ. 30፡15፤19፤ መዝሙር 1)።

▣ **"ከእኔ ራቁ"** መዝ. 6፡8፤119፡115፤ማቴ. 7፡23 ተመልከት። ይህ በትክክል ተቃራኒ ነው ከመዝ. 139፡18ለ ጋር፣ ይኸውም የእግዚአብሔርን ከታማኝ ተከታዮቹ ጋር መገኘት ከሚገልጸው።

ይህ የመጨረሻ አንጓ ባሕርዩ በተተኳሪዎች ነው (ሰባት)። ሌላ ተተኳሪዎች በዚህ መዝሙር ላይ አይገኙም።

1. ከእኔ ራቁ፣ መዝ. 139፡19 – ቢዲቢ 693፣ ኬቢ 747፣ ቃል ተተኳሪ የተመለከተው ለ "ኃጢአተኞች" ነው
2. መርምረኝ፣ መዝ. 139፡23 – ቢዲቢ 350፣ ኬቢ 347፣ ቃል ተተኳሪ፤ተመሳሳይ ሥር መዝ. 139፡1 ላይ ይገኛል፣ ወደ እግዚአብሔር የተመለከተ፣ መዝ. 26፡2፤ቁጥር 2-7 ወደ እግዚአብሔር የተመለከቱ ናቸው፣ በመዝሙረኛው
3. ልቤን ታውቃለህ፣ መዝ. 139፡23 (ሁለቴ) – ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 139፡1፣2፣14 ተመልከት፣ ወደ እግዚአብሔር ነው የተመለከተው
4. ፈትነኝ፣ መዝ. 139፡23 – ቢዲቢ 103፣ ኬቢ 119፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 7፡9፤11፡5
5. ታውቃለህ፣ መዝ. 139፡23 – ከቁ.3 ጋር ተመሳሳይ
6. መዝ. 139፡24 ተመልከት – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ ቃል ተተኳሪ
7. ምራኝ፣ መዝ. 139፡24 – ቢዲቢ 634፣ ኬቢ 685፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 5፡8፤31፡3

**139፡20 "ጠላቶችህም በከንቱ *ስምህን* ይጠራሉ"** "ስምህን" የሚለው በኢታሊክስ/አግድም መጻፉን ተገንዘብ፣ ይህም ማለት በዕብራይስጥ ጽሑፍ የለም ማለት ነው። ጥሬአዊው የዕብራይስጥ ጽሑፍ፣ ሴፕቱዋጂንትን ተከትሎ "ከተሞችህን በከንቱ" የሚል አለው፣ ነገር ግን ይህ ለመረዳት አዳጋች ትርጉም ይመስላል። ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ለዚህ ምንባብ "ሐ" ደረጃ ይሰጠዋል (ማለትም፣ ተገቢ የሆነ ጥርጣሬ)። "በከንቱ መጥራት" የሚለውን ዳግመኛ ማናበብ ይቻላል "በአንተ ላይ በማመጽ" በሚል መልኩ። ርግጠኝነት የሌለው ሰዎቹ የሚያመለክቱት እግዚአብሔርን የማያውቁ ወይም ትዕቢተኛ የሐሰት መምህራን ለመሆናቸው ነው።

**139፡20-22** ይህ የመዝሙረኛው ተገቢ ቁጣ ነው።

**መዝሙር ፡139፡23-24**

[23]አቤቱ፥ መርምረኝ ልቤንም እወቅ
ፍተነኝ መንገዴንም እወቅ
[24]በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ እይ
የዘላለምንም መንገድ ምራኝ።

**139፡24 "በደልንም በእኔ ውስጥ ብታገኝ"** አንዳንዶች ይሄንን የሚተረጉሙት "የአመንዝራዎች መንገድ" በሚል ነው (ቢዲቢ 780 I)። ይህ ሊሆን ይችላል፣ ምክንያቱም "መንገድ" የሚለው ቃል ዳግመኛ "ወደ ፊትና ኋላ መንቀሳቀስ" በሚል ሊናበብ ስለሚችል። ግልጽ የሆነው ነገር፣ ደራሲው ምንም ዓይነት የኃጢአተኞችን ዝንባሌ ወይም ድርጊት አለመፈለጉ ነው፣ መዝ. 139፡19-22 ላይ የተብራሩትን፣ በሕይወቱ ላይ ምንም እንኳ ወዲያውኑ ባይገነዘባቸውም።

ሌላው አማራጭ (ኤቢ፣ ገጽ 285) ይሄንን መዝሙር መመልከት የሚቻልበት፣ ጻድቅ ሰው በአመንዝራነት ሲከሰስ ነው።

▣ **"የዘላለምንም መንገድ"** ይህ ከኃጢአተኞች መንገድ ጋር የሚቃረን ነው (መዝ. 1፡1፣ 4-5)። የእነርሱ መንገድ ያልፋል፣ ነገር ግን የእግዚአብሔርን ፍቃድ መከተል ውጤቱ የዘላለም ሕይወት ነው (መዝ. 16፡11፤ኤር. 6፡16፤18፡15፤ኢዮብ 22፡15)። ይህ የጥንት መንገድ በብሉይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ እምነት እንደ ሕይወት ስልት በሚለው ጽንሰ-ሐሳብ እየጎለበተ መጣ፣ እናም በአኪ ሙሉ ለሙሉ ጎለበተ፣ ለጥንታዊቷ ቤተ-ክርስቲያን መጠሪያነት "መንገድ" በሚል።

“ዘላለም” የሚለው ስም (ቢዲቢ 761) የዕብራይስጥ ኦላም ነው፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (ኦላም)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት *መመሪያ* ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር የዘመናዊውን ሰው ልብ እና ሐሳብ ለምን እጅግ አድርጎ ይይዛል (ይነካል)?
2. ይህ መዝሙር በየዕለቱ ሕይወታችን ስለ እግዚአብሔር የሚለው ምንድነው?
3. የመዝሙር 139፡19-22 አሉታዊ ጽሑፍ ከመጽሐፍ ቅዱሳዊው ደራሲ አጠቃላይ ዓላማ ጋር በምን መልኩ ይገጥማል?

# መዝሙር 140
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጸሎት ከኃጢአተኞች ለመጠበቅ<br>ኤምቲ መግቢያ<br>ለመዘምራን አለቃ የዳዊት መዝሙር | ጸሎት ከክፉ ሰዎች ለመዳን | ጸሎት ከግል ጠላቶች ለመጠበቅ | ጸሎት ለመጠበቅ | በኃጢአተኞች ላይ |
| 140:1-3 | 140:1-3 | 140:1-3 | 140:1-3 | 140:1-3 |
| 140:4-5 | 140:4-5 | 140:4-5 | 140:4-5 | 140:4-5 |
| 140:6-8 | 140:6-8 | 140:6-8 | 140:6-8 | 140:6-8ለ |
| | | | | 140:8ሐ-11 |
| 140:9-11 | 140:9-11 | 140:9-11 | 140:9-11 | |
| 140:12-13 | 140:12-13 | 140:12-13 | 140:12-13 | 140:12-13 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. በርካታ ስሞች ለእግዚአብሔር ጥቅም ላይ ውለዋል፣ እዚህ መዝሙር ላይ።
1. ያህዌ መዝ. 140:1፣4፣6 (ሁለቴ)፣7፣8፣12
2. እግዚአብሔር (ማለትም፣ ኤል)፣ መዝ. 140:6
3. ኣዶን፤ መዝ. 140:7

ለ. የተለያዩ ሰዎች ባሕርይ እንዴት እንደተመለከተ ተገንዘብ
1. ያልታመኑ
   ሀ. ክፉ ሰዎች፣ መዝ. 140፡1ሀ
   ለ. ዓመጸኛ ሰዎች፣ መዝ. 140፡1ለ፣4ለ
   ሐ. በልባቸው ክፉ ነገሮችን የሚያስቡ፣ መዝ. 140:2ሀ
   መ. ጦርነትን የሚያስነሡ፣ መዝ. 140:2ለ
   ሠ. አንደበታቸው እንደ እፉኝት የሰላ፣ መዝ. 140፡3ሀ
   ረ. ከከንፈራቸው በታች የእባብ መርዝ አለ፣ መዝ. 140፡3ለ
   ሰ. ኃጢአተኛ ሰዎች፣ መዝ. 140፡4ሀ
   ሸ. ለማሰናከል ያልማሉ፣ መዝ. 140፡4ሐ
   ቀ. ትዕቢተኞች የተሸሸገ ወጥመድ አላቸው፣ መዝ 140፡5ሀ
   በ. መረባቸውን የዘረጋሉ፣ መዝ. 140፡5ለ
   ተ. ወጥመድ ያበጃሉ፣ መዝ. 140፡5ሐ
2. የእስራኤል መለኮት (አምላክ)
   ሀ. ይታደጋል፣ መዝ. 140:1ሀ
   ለ. ይጠብቃል፣ መዝ. 140:1ለ፣4ለ
   ሐ. ይጠብቃል መዝ. 140:4ሀ
   መ. እሱ ኤል ነው፣ መዝ. 140:6ሀ
   ሠ. ያዳምጣል፣ መዝ. 140:6ለ

ሸ. እሱ የመዳን ኃይል ነው፣ መዝ. 140:7ሀ (እዚህጋ ብቻ ብኪ ላይ)
ቀ. ውጊያ ላይ ጠባቂ ነው፣ መዝ. 140:7ለ
በ. የጎስቋላውን ጉዳይ ይመለከታል፣ መዝ. 140:12ሀ
ተ. ለድሀ ፍርድን ያደርጋል፣ መዝ. 140:12ለ

3. ታማኝ ተከታዮች
ሀ. ጎስቋሎች፣ መዝ. 140:12ሀ
ለ. ደሀ፣ መዝ. 140:12ለ
ሐ. ጻድቅ ምስጋና ያቀርባል፣ መዝ. 140:13ሀ
መ. ቅን ከእግዚአብሔር ጋር ይኖራል፣ መዝ. 140:13ለ

ሐ. ይህ መዝሙር "ሁለቱን መንገዶች" በግልጽ ያመለክታል (ዘዳ. 30:15፣19፤መዝሙር 1)።

መ. ይህ መዝሙር እንደ መዝሙር 139 በርካታ ቁጥር ልዩ ፍች ያላቸው ያልተለመዱ ቃላትን ይዟል።

ሠ. ማሶረቲካዊ ሊቃውንት ሦስት ለውጦችን ያቀርባሉ (ቄሬ) ለኤምቲ፣ አንደኛውም መዝ. 140፡10፣11፣13 ሲሆን ይኸም በጽሑፉ ላይ ያለውን ውዥንብር ያሳያል።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡140፡1-3**
**1-2አቤቱ፥ ከክፉ ሰው አድነኝ፥**
**በልባቸውም ክፉ ካሰቡ**
**ከዓመፀኞች ሰዎች ጠብቀኝ**
**ቀኑን ሁሉ ለሰልፍ ይከማቻሉ።**
**3ምላሳቸውን እንደ እባብ ሳሉ**
**ከከንፈራቸው በታች የእፉኝት መርዝ ነው። ሴላህ።**

**140፡1-3፤4-5** እነዚህ ሁለት አንጓዎች በብዙ መንገዶች ትይዩ ናቸው፣ በተለይም መዝ. 140፡1 እና 4 ለእግዚአብሔር ጸሎት ናቸው። ሁለተኛው ስንኝ ላይ ያሉት ሁለቱም ተተኳሪዎች እንደ ተጽዕኗዊ ነው ጥቅም ላይ የዋሉት፣ ወይም ይልቁንም የጥያቄ ተተኳሪዎች ይሆናሉ። ስለዚህ፣ የመዝሙር 140፡1 የመጀመሪያው ግሥ "ማዳን" (ቢዲቢ 322፣ ኬቢ 321፣ ፒል ተተኳሪ)፣ "መጠበቅ" ከሚለው ጋር ትይዩ ነው (ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ ቃል ተተኳሪ) የመዝ. 140:4።
የሁለተኛው መስመር ሁለቱም መዝ. 140፡1 እና 4 ተመሳሳይ ናቸው።
ኃጢአተኞች ባሕርያቸው መዝ. 140፡2-3 እና 4ሐ-5 ተመልክቷል።

**140፡2 "ክፉ ነገርን ያስባሉ"** ይህ እግዚአብሔርን የማይከተሉ ሰዎች ባሕርይ ነው (መዝ. 7:14፤36:4፤52:2፤
ምሳ. 3:29፤6:14፤ኢሳ. 59:4፤ሆሴ. 7:15፤ሚክ. 2:1፤ናሆ. 1:9)። በሥራቸው አባታቸው ማን እንደሆነ ታውቃላችሁ (ዮሐንስ 8:39-44)! በፍሬአቸው ታውቋቸዋላችሁ (ማቴ. 7:15-23)!
ተመሳሳይ ግሥ፣ "ሐሳብ" (ቢዲቢ 362፣ ኬቢ 359፣ ቃል የተጠናቀቀ) መዝ. 140:4ሐ ላይ ተደግሟል።

▣ **"ልብ"** ይህ የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው ለሙሉ ስብዕና። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ።

▣ **"ቀኑን ሁሉ ለሰልፍ ይከማቻሉ።"** ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ይሄ የሚያመለክተው የግለሰቦችን የከፋ ውዝግብ ነው፣ የመሣርያ ግጭት ሳይሆን፣ በሕዝቦች መካከል (አእት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ቁ. 21፣ ገጽ 1005 ተመልከት)። እሱም ሊሆን የሚችለው መዝሙር 139 የተጻፈው የፍርድ ቤት የጀርባ ትዕይንት (መቼት) በመቃወም ሊሆን ይችላል፣ የአመንዝራነት ክስ፣ እንዲሁ ደግሞ መዝሙር 140 (በተለይም፣ መዝ. 140፡12)።

**140፡3** የቃላቶቹን ቁጥር ተመልከት በ ✓ ሀ ውስጥ ያሉትን (ማለትም፣ የጽምጽ መቀያየር (ጨዋታ)።

1. ግሥ፣ "ሳሉ" (ቢዲቢ 1041)
2. ስም፣ "ምላስ" (ቢዲቢ 546)
3. ስም፣ "እባብ" (ቢዲቢ 638)
4. ስም፣ "እፉኝት" (ቢዲቢ 747)
5. ከንፈራቸው (ቢዲቢ 973)

ሁሉም የሚሉት ከእባብ ሰቅጣጭ ድምጽ ጋር በተያያዘ ነው። ጳውሎስ ይሄንን ቁጥር ሮሜ. 3፡13 ላይ ጠቅሶታል፣ ከብዙዎቹ የብኪ ምሳሌዎች አንዱ እንደሚሆን፣ ስለ ሰው ልጅ ኃጢአት (ሮሜ. 3:9-18፣23)። ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 130:3-4 ላይ።

▣ **"እፉኝት"** ይህ ስም (ቢዲቢ 747፣ עכשוב ) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ። አብዛኞቹ ትርጉሞች "አነስተኛ እባብ" ወይም "እፉኝት" የሚል ሲኖራቸው፣ አንዳንዶቹ ግን (የተእመቅ) "ሸረሪት" የሚል አለው (ቢዲቢ 747፣ עכביש)።

**መዝሙር ፡140፡4-5**

[4]አቤቱ፥ ከኃጢአተኞች እጅ ጠብቀኝ፥
እርምጃዬንም ሊያሰናክሉ ከመከሩ
ከዓመፀኞች አድነኝ።
[5]ትዕቢተኞች ወጥመድን ሰወሩብኝ፥
ለእግሮቼም የወጥመድ ገመድን ዘረጉ
በመንገድ ዕንቅፋትን አኖሩ። ሴላህ።

**140፡4-5** የማደኛ ገመዱን ዘይቤ ተገንዘብ (መዝ. 9፡15፤31፡4፤35፡7፤64፡5፤119፡110፤141፡9-10፤142፡3)።

1. እርምጃዬን ሊያሰናክሉ፣ መዝ. 140፡4ሐ
2. ወጥመድ ሰወሩብኝ፣ መዝ. 140፡5ሀ
3. ገመድ ሰወሩብኝ፣ መዝ. 140፡5ሀ
4. በመንገድ መረብ ዘረጉ፣ መዝ. 140፡5ለ
5. ወጥመድ ዘረጉ

**140፡5፤8 "ሴላህ"** ሙሙሉ ማስታወሻ ተመልከት፣ መዝ. 3፡2 ላይ።

**መዝሙር ፡140፡6-8**

[6]እግዚአብሔርንም። አንተ አምላኬ ነህ
የልመናዬን ቃል፥ አቤቱ፥ አድምጥ አልሁት።
[7]አቤቱ፥ ጌታዬ፥ የመድኃኒቴ ጕልበት፥
በሰልፍ ቀን ራሴን ሸፈንህ።
[8]አቤቱ፥ ከምኞቱ የተነሣ ለኃጢአተኞች አትስጠኝ
በላዬ ተማከሩ እንዳይጓደዱ አትተወኝ። ሴላህ።

**140፡6-7** ይህ የኪዳን ቋንቋ ነው። ታማኝ ተከታዩ ታማኝ አምላኩን ይጠራል፣ እንዲረዳውና እንዲታደገው።
የጸሎት ጥያቄዎቹን ተመልከቱ።

1. አድነኝ፣ መዝ. 140፡1ሀ
2. ጠብቀኝ፣ መዝ. 140፡1ለ
3. ጠብቀኝ፣ መዝ. 140፡4ሀ
4. ጠብቀኝ፣ መዝ. 140፡4ለ
5. አድምጥ፣ መዝ. 140፡6ለ
6. የኃጢአተኞችን ሐሳብ አታጽና፣ መዝ. 140፡8ሀ
7. ክፉ ሐሳባቸው አይከናወን፣ መዝ. 140፡8ለ
8. የከንፈራቸው ክፋት ይክደናቸው፣ መዝ. 140፡9ለ
9. የእሳት ፍም በላያቸው ይውደቅ፣ መዝ. 140፡10ሀ
10. ወደ እሳት ይጣሉ፣ መዝ. 140፡10ለ
11. እንዳይነሡም ወደ ጥልቅ ጉድጓድ ይጣሉ፣ መዝ. 140፡10ሐ
12. ሐሰት ተናጋሪ ሰው አይጸናም፣ መዝ. 140፡11ሀ
13. ዓመጸኛን ሰው ክፋት ለጥፋት ይፈልገዋል፣ መዝ. 140፡11ለ

እነዚህ የተተኳሪዎች፣ ያልተጠናቀቁ ድብልቆች ናቸው፣ እንደ ተተኳሪ፣ ያልተጠናቀቁዎች ጥቅም ላይ የዋሉ፣ እንደ ተጽዕኖዊና ተጽዕኖዊዎች ጥቅም ላይ የዋሉ። ይህ መዝሙር ለፍርድ የሚሆን ጸሎት ነው፣ በክፉዎች፣ ዓመጸኞች፣ ትዕቢተኞች፣ ውሸታም ሰዎች ላይ እንዲደረግ!

**140፡8 "ሐሳብ"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 16) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ። መዝሙረኛው ይጸልያል የክፉዎች "ሐሳብ" እንዳይፈጸም። እግዚአብሔር የታማኝ ተከታዮችን የልብ "መሻት" ይሰጣል፣ ምክንያቱም እዚያ ስላስቀመጣቸው። የእኛ "መሻቶች" (እና የእኛ ቃላት) ልባችንን አጥርቶ ይገልጣል!

▣ **"ብልሃት"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 273) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ።

**መዝሙር ፡140፡9-11**

[9]የሚከብቡኝን ራስ
የከንፈራቸው ክፋት ይክደናቸው።
[10]የእሳት ፍም በላያቸው ይውደቅ
እንዳይነሡም ወደ እሳትና
ወደ ማዕበል ይጣሉ።
[11]ተናጋሪ ሰው በምድር ውስጥ አይጸናም

ዓመፀኛን ሰው ክፉት ለጥፋት ይፈልገዋል።

**140፡9 "ራስ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ 910) የሚያመለክተው (1) የኃጢአተኞች፣ ዓመጸኞች፣ ውሸታሞች፣ ትዕቢተኞች ሰዎች መሪ ወይም አደራጅ፣ እነርሱም በመዝሙረኛው ላይ የሚያሴሩ ወይም (2) ድል አድራጊ የመሆን ፈሊጥ። ቁጥር 2 ከዐውደ-ጽሑፉ ጋር በተሻለ ይገጥማል። በርካታ "የወል ነጠላ ቁጥሮች" እዚህ መዝሙር ላይ አሉ።

**140፡10 "እሳት"** ይህ የፍርድ ተምሳሊት ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ እሳት።

▣
**አአመመቅ፣ አኪጀቅ** **"ጥልቅ ጉድጓዶች"**
**አየተመቅ፣ አእቅ፣**
**ጄፒኤስአኤ** **"ጉድጓዶች"**
**አኢመቅ** **"ረግረግ"**
**የተእመቅ** **"ረግረጋማ አዘቅት"**

ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ. 243) እዚህ ጋ ብቻ ነው የሚገኘው። ቢ.ዲ.ቢ. "ውኃማ ጉድጓድ" ወይም "ጎርፍ" የሚል ትርጉም አለው። ለውኃ እንደ ጥንታዊ የሁከት ተምሳሊት፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ውኆች።

ደግሞም ሊሆን የሚችለው የዚህ ቁጥር ምናባዊ ምስያ የሚያመለክተው የእሳት ሲኦልን ነው (ዘዳ. 32፡22)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሲኦል።

**140፡11 "ፈጥነው"** ይህ ቃል (ቢ.ዲ.ቢ 191) እዚህጋ ብቻ ነው፣ ብኪ ላይ የሚገኘው። እሱም የሚለው "በምት ላይ ምት፣" ነው፣ ስለዚህ እሱ ዓመጽን ያመለክታል። ኒዶቴ፣ ቅጽ 1 ገጽ 934 የሚለው "በፍጥነት" የሚያመለክተው "ሐሰተኛ በአገሩ ላይ ከመመቻቸቱ በፊት ይጠፋል" የሚል ነው (ማለትም፣ የተስፋይቱ ምድር)።

**መዝሙር ፡140፡12-13**
[12]**እግዚአብሔር ለድሀ ዳኝነትን**
**ለችግረኛም ፍርድን እንዲያደርግ አወቅሁ።**
[13]**ጻድቃንም በእውነት ስምህን ያመሰግናሉ**
**ቅኖችም በፊትህ ይኖራሉ።**

**140፡12 "ችግረኛ... ደሀ"** እነዚህ ዘወትር በመዝሙር ጥቅም ላይ ይውላሉ፣ ለታማኝ ተከታዮች (መዝ. 9፡18፤ 34፡6፤40፡17፤70፡5፤86፡1፤109፡22)። ይህ የኢየሱስ ምናባዊ ምስያ መነሻ ሊሆን ይችላል፣ የማቴ. 5፡3-4።

**140፡13 "ስምህ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ።

▣ **"በፊትህ ይኖራሉ"** ይህ ሊያመለክት የሚችለው
1. በመቅደስ አምልኮ
2. ከዚህ ሕይወት በኋላ፣ ከእግዚአብሔር ጋር

ዐውደ-ጽሑፍ ብቻ ነው መናገር የሚችለው፤ መዝ. 11፡7፤16፡11፤17፡15፤23፡6፤31፡20 ተመልከት።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ከመዝሙር 139 ጋር እንዴት ሊዛመድ ይችላል?
2. ኃጢአተኞች የተገለጹበትን መንገዶች ዘርዝር።
3. መዝሙር 140፡6 እና 7 እንደ መዝሙረኛው የእምነት መግለጫ ተደርገው ለምን ይወሰዳሉ?
4. "ችግረኛ" እና "ደሀ" የሚሉት ቃላት የትኞቹን ቡድኖች ነው የሚያመለክቱት?
5. መዝ. 140፡13ለ የሚያመለክተው የመቅደስ አምልኮን ነው ወይስ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር መሆንን?

# መዝሙር 141
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የሌሊት ጸሎት ለመቀደስና ለመጠበቅ<br><br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር። | ጸሎት ከክፉት ለመጠበቅ | ጸሎት ከግል ጠላቶች ለመዳን (ሰቆቃ) | የሌሊት ጸሎት | የክፉውን ማራኪነት በመቃወም |
| 141:1-4 | 141:1-2 | 141:1-2 | 141:1-2 | 141:1-2 |
| | 141:3-4 | 141:3-4 | 141:3-4 | 141:3-4ለ |
| | | | | 141:4ሐ-5 |
| 141:5-7 | 141:5ሀ-ሠ | 141:5-7 | 141:5-7 | |
| | 141:5ረ-7 | | | |
| | | | | 141:6-7 |
| 141:8-10 | 141:8-10 | 141:8-10 | 141:8-10 | 141:8-9 |
| | | | | 141:10 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የተዘጋጀው በሌሊት የአምልኮ ሰዓት በመቅደስ ነው (መዝ. 141፡2)።

ለ. እንደ መዝሙር 139 እና 140፣ ይህ መዝሙር የሕግ ቃላትን ይጠቀማል።
1. መዝሙረኛው አይናገር (መዝ. 141፡3)
2. ኃጢአተኞቹ ሁለቱም ናቸው (መዝ. 141፡6)
   ሀ. ፈራጆች
   ለ. ምስክሮች

ሐ. የአደን ምናባዊ ምስያ እንደገና ለመዝሙረኛው አሳዳጆች ጥቅም ላይ ውሏል /መዝ. 140፡4-5/፡፡
1. ወጥመድ፣ መዝ. 141፡9ሀ
2. ወጥመዶች፣ መዝ. 141፡9ለ
3. መረብ፣ መዝ. 141፡10ሀ

መ. ይህ መዝሙር በጸሎት ጥያቄዎች የተሞላ ነው (ተተኳሪዎች/ተጽዕኗዊዎች)።
1. ለመዝሙረኛው
   ሀ. ወደ እኔ ፍጠን፣ መዝ. 141:1ሀ – ቢዲቢ 301፣ ኬቢ 300፣ *ቃል ተተኳሪ*
   ለ. አድምጥ፣ መዝ. 141:1ለ – ቢዲቢ 24፣ ኬቢ 27፣ *ሂፊልተተኳሪ*
   ሐ. ጸሎቴን ተቀበልልኝ፣ መዝ. 141:2ሀ – ቢዲቢ 465፣ ኬቢ 464፣ *ኒፋል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ*
   መ. ለአፌ ጠባቂ አኑር፣ መዝ. 141:3ሀ – ቢዲቢ 1011፣ ኬቢ 1483፣ *ቃል ተተኳሪ*
   ሠ. የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ፣ መዝ. 141:3ለ – ቢዲቢ 665፣ ኬቢ 718፣ *ቃል ተተኳሪ*፤“መዝጊያ” የሚለው ቃል (ቢዲቢ 194) እዚህ ጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ

ረ. ልቤን ወደ ክፉ ነገር አትመልሰው፣ መዝ. . 141፡4ሀ – ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ ሂፊልተጽዕኗዊ
ሰ. ጻድቅ በምሕረት ይገሥጸኝ፣ መዝ. 141፡5ሀ – ቢዲቢ 240፣ ኬቢ 249፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
ሸ. ጻድቅ ይዝለፈኝም፣ መዝ. 141፡5ሀ – ቢዲቢ 406፣ ኬቢ 410፣ ሂፊልያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
ቀ. ራሴም እንዳይቀበለው አትተው፣ መዝ. 141፡5c – ቢዲቢ 626፣ ኬቢ 677፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
በ. ያለ ረዳት አትተወኝ፣ መዝ. 141፡8ለ – ቢዲቢ 788፣ ኬቢ 881፣ ፒል ተጽዕኗዊ
ተ. ከወጥመድ መንጋጋ ጠብቀኝ፣ መዝ. 141፡9ሀ – ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ ቃል ተተኳሪ
ቸ. በሰላም ልለፍ፣ መዝ. 141፡10ለ – ቢዲቢ 716፣ ኬቢ 778፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

2. ለኃጢአተኞች
   ሀ. ጸሎቴ በክፉ ሥራቸው ላይ ነው
      (1) ፈራጆቻቸው ይጣሉ፣ መዝ. 141፡6ሀ
      (2) አጥንቶቻቸው በሲኦል ተበተኑ፣ መዝ. 141፡7ለ
   ለ. ኃጢአተኞች በወጥመዳቸው ይውደቁ፣ መዝ. 141፡9ለ – ቢዲቢ 656፣ ኬቢ 709፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ (ማለትም፣ የሚና ተገላቢጦሽ)

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡141፡1-4**

**[1]አቤቱ፥ ወደ አንተ ጮኽሁ ስማኝ**
**ወደ አንተ ስጮኽም የልመናዬን ቃል አድምጥ።**
**[2]ጸሎቴን በፊትህ እንደ ዕጣን ተቀበልልኝ፥**
**እጅ መንሣቴም እንደ ሠርክ መሥዋዕት ትሁን።**
**[3]አቤቱ፥ ለአፌ ጠባቂ አኑር፥**
**የከንፈሮቼንም መዝጊያ ጠብቅ።**
**[4]ልቤን ወደ ክፉ ነገር አትመልሰው፥**
**ዓመፃን ከሚያደርጉ ሰዎች ጋር**
**ለኃጢአት ምክንያት እንዳልሰጥ**
**ከምርጦቻቸውም ጋር አልተባበር።**

**141፡2ሀ** መዝሙር ላይ እንዲህ ዓይነት ቁጥሮች ለይሁዲነት ይፈቅዳል፣ አምልኳቸውን ለማስረገጥ (ማለትም፣ ያለ መቅደስ፣ እና ስለዚህ፣ ያለ ምንም ታሳቢ መሥዋዕት) በያህዌ ተቀባይነት ያገኛል። ጸሎትና ምስጋና ናቸው አሁን መሥዋዕቶቹ።

**141፡2ለ "እጆቼን ማንሣቴም"** ይህ ተገቢው አቋቋም ነው፣ ለአይሁድ ጸሎት።
1. መቆም
2. ራስን ማቅናት (ማለትም፣ ወደ እግዚአብሔር መመልከት)
3. እጅን ማንሣት (ማለትም፣ እንደ መቀበል ያለ)
4. ዓይኖች ተገልጠው (ማለትም፣ ከእግዚአብሔር ጋር በመነጋገር)

▣ **"የሠርክ መሥዋዕት"** የመሥዋዕታዊው ሥርዓት ከፊል የነበረው በየማለዳው በመቅደስ የበግ መሥዋዕት ማቅረብ ነበር፣ 3፡00 ሰዓት ላይ (መዝ. 5፡3) እና በምሽት 9፡00 ሰዓት ላይ (ዘጸ. 29፡38-46፤ዘኍ. 28፡1-8)። ይኸም ልዩ የጸሎት ሰዓት ሆኗል (ማለትም፣ ሐዋ. 3፡1፤10:30)።

**141፡3** አንዱ ሊደነቅ ይችላል የዚህ ቁጥር ፍሬ-ሐሳብ ምን ሊሆን በመቻሉ።
1. የፍርድ-ቤት ትዕይንት
2. ሹክሹክታ
3. በአሳዳጆች ላይ የቃል ጥቃት

ሁለቱን ትይዩዎች ተገንዘብ ቃል ተተኳሪ ("ጠባቂ አኑር፤" "ጠባቂ አድርግ")።

**141፡4ሀ** ይህ ቁጥር ለእግዚአብሔር ሉዓዊነት እውቅና መስጠት ነው። ዘመናዊዎች መጠንቀቅ ይገባቸዋል፣ ይሄንን ወዲያውኑ ከማየት፣ ከካልቪናዊ እና አርሚኒያን ክርክር አኳያ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዕጣ-ፈንታ [ካልቪናዊነት] በተቃርኖ የሰዎች ነጻ ፍቃድ [አርሚናዊነት])።

ይህ የዕብራይስጥን ርዕዮተ-ዓለም ያንጸባርቃል። አምላካቸው ሁሉንም ነገር ይቆጣጠራል (መክ. 7፡14፤ኢሳ. 45፡7፤ሰቆ. 3፡38፤አሞጽ 3፡6ለ)። ይሄንን የመሰሉ ዓረፍተ-ነገሮች ነጻ ፍቃድን ወይም የሰዎች ድርጊት አስፈላጊነትን ዋጋ ቢስ እንደሚያደርጉ ተደርጎ መወሰድ የለበትም፣ ነገር ግን ለአንዱ እውነተኛ አምላክ እውቅና መስጠት እንጂ (ማለትም፣ ሁሉም ለእግዚአብሔር አስተዋጽዖ የሚሰጡ ናቸው፣ ምንም ሁለተኛ ምክንያት ሳይኖር)።

"አዘንብል" የሚለው ግሥ (ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ ሂፊል ተጽዕኗዊ) ጥቅም ላይ የዋለው በኪዳናዊ መልኩ ነው 1 ነገ. 8፡58፤መዝ. 119፡36። ለዚህ መልካም ትይዩ ምሳ. 1፡8-19 ተመልከት። የልብ መሻት እውነተኛ ሰውን ይገልጣል።

▣ በርግጠኝነት ክፉ አለ (ቢዲቢ 948) እና ዓመጸኝነት፣ በዓለም ላይ። ታማኝ ተከታይ ከእሱ ይሸሻል፣ እሱን ከሚያደርጉትም።

▣ **"ከጣፋጭ ምግባቸው እንድመገብ አይሁን"** ይህም ሌላው ያልተጠናቀቀ ነው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ። እሱ ርግጠኝነት አይኖረውም፣ ይህ የሚጠቅስ ከሆነ

1. ማኅበራዊ ሁነት
2. በኃጢአት የተሞላ የሕይወት ስልት
3. የጣዖት አምልኮ መቼት፤ ማለት የሚቻለው ሁለቱም መዝሙር 139 እና 140 ከጣዖት አምልኮ ማብራሪያዎች ጋር እንደሚዛመዱ ነው

***መዝሙር ፤141፤5-7***

**5ጻድቅ በምሕረት ይገሥጸኝ፥ ይዘለፈኝም፥**
**የኃጢአተኛ ዘይት ግን ራሴን አይቅባ**
**ጸሎቴ ገና በክፋታቸው ላይ ነውና።**
**6ኃያላኖቻቸው በዓለት አጠገብ ተጣሉ**
**ጣፋጭ ናትና ቃሌን ይሰማሉ።**
**7በምድር ላይ እንደ ተሰነጠቀ እንደ መሬት ጓል፥**
**እንዲሁ አጥንቶቻችን በሲኦል ተበተኑ።**

**141፡5** ይህ ቁጥር ምሳሌ ላይ ያለ ተደጋጋሚ ጭብጥን ያንጸባርቃል (ምሳ. 9፡8፤19፡25፤25፡12፤ደግሞም መክ. 7፡5 እይ)። ከጻድቅ ሰው የሆኑ ተግሣጽና እርምቶች የእግዚአብሔር ጥበብ ላላቸው የከበሩ ስጦታዎች ናቸው።

መዝሙር 141፡5 ሦስት ያልተጠናቀቁ አሉት፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ።

1. *መገሠጽ* – ቢዲቢ 240፣ 249፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
2. *መዝለፍ* – ቢዲቢ 406፣ ኬቢ 410፣ *ሂፊል*ያልተጠናቀቀ
3. *አሌ ማለት* (እምቢ) – ቢዲቢ 626፣ ኬቢ 677፣ *ሂፊል* ተተኳሪ

የጸሎት ጥያቄዎቹ እነዚህ ናቸው!

▣ **"ዘይት የተቀባ ራስ"** አየተመቅ፣ አእቅ፣ አኢመቅ፣ እና የተእመቅ፣ LXXን ተከትለው፣ "የኃጢአተኛ ዘይት ግን ራሴን አይቅባ" የሚል አላቸው። መዝሙር 141፡5-7 በዕብራይስጥ እጅግ አስቸጋሪ ነው። በርካታ ወጣ ያሉ ትርጉሞች አሉ። የተሻለ የሚሆነው አጠቃላይ ስሜቱን አግኝቶ ወደ ቀጣዩ አንጓ መንቀሳቀስ ነው!

▣ **"በምሕረት"** ይህ ጠቃሚ የኪዳን ቃል ነው፣ *ሄሰድ*። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት (ሄሰድ)።

▣ የመጨረሻው የቅኔ ስንኝ (መስመር) ከስፍራው ወጣ ያለ ይመስላል፣ ከቀዳሚዎቹ አራት ስንኞች ጋር በተገናኘ። አኪጀት ቀጣዩን አንጓ የሚጀምረው (መዝ. 141፡5-7) በእርሱ ነው።

አየተመቅ፣ አእቅ፣ እና ጀፒኤስኦኤ የግርጌ ማስታወሻ አላቸው፣ ይኸውም መዝ. 141፡5፣6፣7 ርግጠኛ ላለመሆናቸው።

**141፡6 "ዓለት"** ይህ ማለት የሚሆነው

1. ለሞታቸው ማጣቀሻ (2 ዜና. 25፡12)
2. የያህዌ መጠሪያ (ማለትም፣ "ዓለቱ፣" ዘዳ. 32፡18፤መዝ. 18፡2፣31፣46፤19፡14፤28፡1፤31፡3፤42፡9፤71፡3፤አአመቅ እና አኢመቅ ትርጉሞችን ተመልከት)

**141፡7 "የሲኦል ደጅ"** የብኪ የሙታን ማቆያ ስፍራ በሰውኛ ዘይቤ ተቀምጧል፣ እንደሚበላ አውሬ ተቀምጧል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሲኦል)።

***መዝሙር ፤141፤8-10***

**8አቤቱ ጌታ፥ ዓይኖቼ ወደ አንተ ናቸውና**
**በአንተ ታመንሁ፥ ነፍሴን አታውጣት።**
**9ከሰወሩብኝ ወጥመድ፥**
**ዓመፅንም ከሚያደርጉ ሰዎች ዕንቅፋት ጠብቀኝ።**
**10እኔ ብቻዬን እስካልፍ ድረስ**
**ኃጢአተኞች በወጥመዳቸው ይውደቁ።**

**141፡8ሀ** ይህ የመዝሙረኛው የእምነት ማረጋገጫ ነው፣ በእስራኤል የኪዳን አምላክ። ለ"ያህዌ" እና "አዶን" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

**141፡8ለ "መታመኛ"** ይህ የተለመደ ግሥ ነው (ቢዲቢ 340፣ ኬቢ 337፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) መዝሙር ላይ። መዝ. 2፡12 ላይ ማስታወሻ ተመልከት፣ በድረ-ገጽ (www.freebiblecommentary.org)።

▣ ሁለተኛው ግሥ (ቢዲቢ 788፣ ኬቢ 881፣ *ፒል* ተጽዕኗዊ) መሠረታዊ ፍችው "እራቁት መሆን" ወይም "ገላጣ መሆን" ነው (ማለትም፣ መጋለጥ)። ቢዲቢ እና ኬቢ የሚያስረግጡት እዚህ፣ እና እዚህ ብቻ ፍችው "መፍሰስ" ነው (እሱም የመሥዋዕት ፍች ያለው፣ ሂፊል መልኩን ኢሳ. 53፡12 ላይ ተመልከት)።

▣ **"እኔ"** ይህ የዕብራይስጥ ኔፊሽ ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 659)፣ እሱም ሙሉ ቁመና ሰውን የሚገልጽ። ዘፍ. 35፡18 ላይ ማስታወሻ ተመልከት፣ በድረ-ገጽ።

**141፡9-10** ይህ ከእስራኤል የአደን ብልሃት ምናባዊ ምስያ ነው፣ ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 140፡4-5።

1. ወጥመድ (ቢ.ዲ.ቢ. 809)
2. ወጥመዶች (ቢ.ዲ.ቢ. 430)
3. መረቦች (ቢ.ዲ.ቢ. 485፣ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ነገር ግን ለ "መረብ" ሌላ ቃል [ቢ.ዲ.ቢ. 440] መዝ. 140፡5 ላይ ይገኛል)

**141:10 "ኃጢአተኞች በወጥመዳቸው ይውደቁ።"** ሰዎች የዘሩትን ያጭዳሉ! ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መርሕ ነው፣ በተደጋጋሚ የሚገለጽ (ኢዮብ 34:11፤መዝ. 28:4፤62:12፤ምሳ. 24:12፤መክ. 12:14፤ኤር. 17:10፤32:29፤ማቴ. 16:27፤25:31- 46፤ሮሜ. 2:6፤14:12፤1 ቆሮ. 3:8፤2 ቆሮ. 5:10፤ገላ. 6:7፤2 ጢሞ. 4:14፤1 ጴጥ. 1:17፤ራዕ. 2:23፤20:12፤22:12)።

**"እኔ በሰላም እስካልፍ ድረስ"** ይህ ቁጥር የሚጠበቀውን "የሁለቱን መንገዶች" ውጤት ይገልጻል (ዘዳ.
30:15፣19፤መዝሙር 1)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝ. 141፡2 ለይሁዲነት እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድነው?
2. መዝ. 141፡3 እና 4 ዕጣ ፈንታን ይደግፋሉን?
3. መዝ. 141፡4መ ምንን ነው የሚጠቅሰው
4. መዝ. 141፡5-7 በሙሉ ስለ ኃጢአተኞች ነውን?
5. "ዓለቱ" መዝ. 141፡6ሀ ምን ማለት ነው?
6. "ሁለቱን መንገዶች" ግለጽ። መዝ. 141፡10 እንዴት ይሄንን የብኪ ሥነ-መለኮታዊ እሳቤ ይጠቅሳል?

# መዝሙር 142
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የዕርዳታ ጸሎት በችግር ጊዜ | ከስደት ለማረፍ ጸሎት | ከግል ጠላቶች ለመጠበቅ ጸሎት | የዕርዳታ ጸሎት | ጸሎት በስደት ጊዜ |
| ኤምቲ መግቢያ | | (ሰቆቃ) | | |
| የዳዊት ትምህርት፣ በዋሻ ውስጥ በነበረ ጊዜ። ጸሎት። | | | | |
| 142:1-4 | 142:1-2 | 142:1-3ለ | 142:1-4 | 142:1-3ለ |
| | 142:3-4 | | | |
| | | 142:3ሐ-4 | | 142:3ሐ-4 |
| 142:5-7 | 142:5-7 | 142:5-6ለ | 142:5-7 | 142:5-6ለ |
| | | 142:6ሐ-7 | | 142:6ሐ-7 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡142፡1-4**
**1በቃሌ ወደ እግዚአብሔር ጮኽሁ**
**በቃሌ ወደ እግዚአብሔር ለመንሁ።**
**2ልመናዬን በፊቱ አፈስሳለሁ**
**መከራዬንም በፊቴ እናገራለሁ።**
**3ነፍሴ በውስጤ ባለቀች ጊዜ**
**መንገዴን አወቅሁ**
**በምሄድባት በዚያች መንገድ**
**ወጥመድን ሰወሩብኝ።**
**4ወደ ቀኝ ተመለከትሁ አየሁም፥**
**የሚያውቀኝም አጣሁ**
**መሸሸጊያም የለኝም፥**
**ስለ ነፍሴም የሚመራመር የለም።**

**142፡1-2** ይህ መዝሙር የሚጀምረው በአራት ያልተጠናቀቁ ነው፣ ቀጣይነት ያለውን ጸሎት በሚጠቅሱ።
1. ጮኽኩ – ቢ.ዲ.ቢ 277፣ ኬቢ 277፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ
2. ልመናዬን አቀረብኩ – ቢ.ዲ.ቢ 335፣ ኬቢ 334፣ *ሂዝፔል* ያልተጠናቀቀ
3. ልመናዬን አፈስሳለሁ – ቢ.ዲ.ቢ 1049፣ ኬቢ 1629፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ፣ 1 ሳሙ. 1:15፤መዝ. 62:8፤ሰቆ. 2:19
4. መከራዬንም እናገራለሁ – ቢ.ዲ.ቢ 616፣ ኬቢ 665፣ *ሂፊል*ያልተጠናቀቀ

**142:3 "ነፍሴ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል *ሩሀ* ነው (ቢ.ዲ.ቢ 924)፣ እሱም "ነፋስ"ን፣ "እስትንፋስ"ን፣ ወይም "መንፈስ"ን የሚገልጽ። እሱም አምላክ-ሰጥ የሆነውን የሰው የሕይወት ኃይልን ለማገለጽ ጥቅም ላይ ይውላል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ

መዝሙረኛው ግራ ተጋብቷል፣ በከሳሾቹ ጥቃት (ማለትም፣ ወጥመድ በሸሸጉበት፣ መዝ. 142:3መ፣ መዝ. 140:4-5፤141:9-10፤ደግሞም "አሳዳጆች" ተብለው ይጠራሉ መዝ. 142:6ሐ ላይ)።

መዝሙረኛው ያስረግጣል፣ ያህዌ እንደሚያውቀው (ማለትም፣ መንገዱን፣ የሚጓዝበትን፣ መዝ. 142:3ለ፣ሐ እና መዝሙር 139) ነገር ግን እንደዛ የሆነ አይመስልም (ማለትም፣ መዝ. 142:4)።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀቅ** ***"መረታት"***

**አየተመቅ፣ አኢመቅ፣**

**የተእመቅ** ***"መዛል"***

**LXX** ***"ዛልኩኝ"***

**ጀፒኤስአኤ** ***"በውስጤ ዛለብኝ"***

ይህ *ሂዝፔል* ያልተጠናቀቀ አወቃቀር (ቢዲቢ 742 III) በመሠረቱ ፍችው "መድከም" ወይም "መዛል" ነው።

1. መድከም – *ሂፊል*፣ ዘፍ. 30:42
2. መዛል – *ቃል*፣ መዝs. 61:3፤ኢሳ. 57:16
3. መዛል – *ሂዝፔል፣* መዝ. 77:4፤107:5፤143:4፤ሰቆ. 2:12፤ዮናስ 2:7

እሱም የመቸገርና ተስፋ የመቁረጥ ፈሊጥ ነው።

▣ ስንኝ/መስመር ለ እና ሐ የሚገልጹት እግዚአብሔር ከታማኝ ተከታዮቹ ሕይወት ጋር እጅግ እንደሚጎዳኝ ነው። ስለምን ችግሮች፣ ሕማም፣ ተቀባይነት ማጣት፣ እና ጥቃቶች እንደሚመጡ ምሥጢር ነው (ማለትም፣ ኢዮብ)፣ ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያስተምረው ያህዌ ለእኛ፣ ከእኛ ጋር ነው፣ እናም ፈጽሞ አይተወንም። ሁኔታዎችን መጋፈጥ እንችላለን፣ በእሱ ላይ ባለን እምነት!

**142፡4** መዝሙረኛው ተደንቋል፣ ማንም ለዕርዳታ ወደ እርሱ ስላልመጣ (መዝሙር 142፡4)፣ ያህዌ እንኳ ቢሆን። ተተኳሪዎቹን ተመልከት።

1. ተመልከት – ቢዲቢ 613፣ ኬቢ 661፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
2. እይ – ቢዲቢ 906፣ ኬቢ 1157፣ *ቃል ተተኳሪ*

መስመር መ እጅግ ያሳዝናል! ብቸኝነት ተሰምቶታል፣ ብቸኝነት! የእርሱ ሁኔታ ተስፋ አስቆራጭ እንደሆነ ተሰምቶታል (ማለትም፣ ኢዮብ)!

LXX ባጠቃላይ የሙባጥን (ሙት ባሕር ጥቅሎች) ይዘት በመከተል፣ ተተኳሪዎችን በቀላል ዓረፍተ-ነገር ያደርጋል፣ "እመለከታለሁ... አያለሁ፣" ያህዌን የሚጠቅስ ሳይሆን፣ መዝሙረኛውን እንጂ። ይህም የአራምኛ ታርጉምን እና ቫልጌትን ተከትሎ ነው። እንደሚመስለኝ ተተኳሪዎቹ ከዐውደ-ጽሑፉ ጋር በተሻለ ይገጥማሉ (ማለትም፣ መዝሙረኛው ለእግዚአብሔር ነው የሚያቀርበው፣ መዝ. 142፡1-3)።

▣ **"ነፍስ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል *ኔፊሽ* ነው፤ ማስታወሻ ተመልከት፣ ዘፍ. 35፡18 ላይ።

▣ **"ስለ ነፍሴም የሚመራመር የለም።"** አንቀጹ (ቢዲቢ 205፣ ኬቢ 233፣ *ቃል* አንቀጽ) በጥሬው "መፈለግ" ነው፣ እናም ሐረጉ ሊተረጎም ይችላል "ማንም ስለ ነፍሴ የሚፈልግ የለም" በሚል፣ ነገር ግን ይህ በእንግሊዝኛ በቀላሉ ተዛብቶ ሊረዳ ይችላል። ስለዚህ አአመመቅ ፍችውን በተሻለ ይዞታል።

***መዝሙር ፡142፡5-7***

**5አቤቱ፥ ወደ አንተ ጮኽሁ።**
**አንተ ተስፋዬ ነህ፥**
**በሕያዋንም ምድር አንተ እድል ፈንታዬ ነህ አልሁ።**
**6እጅግ ተቸግሬአለሁና**
**ወደ ልመናዬ አድምጥ**
**በርትተውብኛልና**
**ከሚያሳድዱኝ አድነኝ።**
**7አቤቱ፥ ስምህን አመሰግን ዘንድ**
**ነፍሴን ከወህኒ አውጣት**
**ዋጋዬን እስከትሰጠኝ ድረስ**
**ጻድቃን እኔን ይጠብቃሉ።**

**142፡5** ይህ የመዝሙረኛው የእምነት ማጽኛ ነው።

1. አንተ መታመኛዬ ነህ
2. በሕያዋን ምድር አንተ ዕድል ፈንታዬ ነህ (ማለትም፣ ከዚህ ሕይወት በኋላ ያለውን ሕይወት እንዳልሆነ ተመልከት፣ ኢዮብ 28:13፤ መዝ. 27:13፤52:5፤116:9፤ኢሳ. 38:11፤ኤር. 11:19)

▣ ***"መታመኛ"*** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መታመኛ (ብኪ)።

▣ **"እድል ፈንታዬ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 16፡5 ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ላይ።

**142፡6-7** ተለጣጣቂ የሆኑ የጸሎት ጥያቄዎች አሉ (*ሂፊል ተተኳሪ*)።

1. ተመልከት – ቢዲቢ 904፣ ኬቢ 1151፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

2. አድነኝ – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ *ሂፊል ተተኳሪ*
3. አውጣኝ – ቢዲቢ 422፣ ኬቢ 425፣ *ሂፊል ተተኳሪ*

**142:7 "ከወኅኒ አውጣት"** ይህ መሆን ያለበት
1. ግራ ለመጋባቱና ለውርደቱ ዘይቤ (መዝ. 142:3-4፣6-7)
2. ወደ ግዞት በኃይል ለተወሰደ ማጣቀሻ
3. የሲኦል ፈሊጥ

"ወኅኒ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 689) ፍችው
1. "እግር ብረት ሠራተኛ" ወይም "ብረት ሠራተኛ" – 2 ነገ. 24:14፤ኤር. 24:1፤29:2
2. ወኅኒ (ሦስት ጊዜ ብቻ ብኪ ላይ)
   ሀ. በጥሬው የፍጻሜ ዘመን ከምድር በታች ወኅኒ (1 ሔኖክ 10.4፣12)
   ለ. ዘይቤአዊ – ኢሳ. 42:7

▣ **"ስምህን አመሰግን ዘንድ"** ይህ በኢየሩሳሌም የሚገኘውን መቅደስ ለመጎብኘት ልመና ነው። ይህም በቀጣዩ መስመር ይጠናከራል፣ "ጻድቃን ዙሪያዬን ይከብባሉ" (ማለትም፣ በአንድነት አምልኮ ላይ)።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝሙረኛው ያህዌ እንደሚያውቀው ያስረግጣል (መዝሙር 142፡3ለ፣ ሐ)፣ ነገር ግን ላለበት ሁኔታ ጥያቄ ያነሣል! የተለመደ ይመስላልን? የእግዚአብሔር መገኘትና ከብካቤ ችግሮችን፣ ሕማምን፣ እና ከፉ ሰዎችን ከሕይወታችን ያስወግዳልን?
2. መዝ. 142፡4 በወዳጆች፣ እና በቤተሰብ ወይም በእግዚአብሔር ስለ መተው ነውን?
3. "ወኅኒ" መዝ. 142፡7 ላይ ስለ ምንድነው የሚጠቅሰው?
4. መዝ. 142፡7 የሚጠቅሰው የመቅደስ አምልኮን ነውን?

# መዝሙር 143
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ለመዳንና ለምሪት ጸሎት<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር። | ልባዊ ጸሎት ለምሪትና ለመዳን | ከግል ጠላቶች ለመጠበቅ ጸሎት<br>(ሰቆቃ) | የእርዳታ ጸሎት | የትሕትና ልባዊ ጸሎት |
| 143:1-4 | 143:1-2 | 143:1-2 | 143:1-2 | 143:1-2 |
| | 143:3-4 | 143:3-4 | 143:3-4 | 143:3-4 |
| 143:5-6 | 143:5-6 | 143:5-6 | 143:5-6 | 143:5-6 |
| 143:7-9 | 143:7-8 | 143:7-8 | 143:7-8 | 143:7 |
| | | | | 143:8 |
| | 143:9-10 | 143:9-10 | 143:9-10 | 143:9-10 |
| 143:10-12 | | | | |
| | 143:11-12 | 143:11-12 | 143:11-12 | 143:11-12 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጕመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. በርካታ ተተኳሪዎች እና ተጽዕኗዊ ጥያቄዎች አሉ።
1. ስማ፣ መዝ. 143፡1ሀ
2. አድምጥ፣ መዝ. 143:1ለ
3. ወደ ፍርድ አትግባ፣ መዝ. 143:2ሀ
4. ፈጥነህ ስማኝ፣ መዝ. 143:7ሀ
5. ፊትህን ከእኔ አትመልስ፣ መዝ. 143:7ለ
6. አሰማኝ፣ መዝ. 143:8ሀ
7. አስተምረኝ፣ መዝ. 143:8ሐ
8. አድነኝ፣ መዝ. 143:9ሀ
9. አስተምረኝ፣ መዝ. 143:10ሀ
10. ቅዱስ መንፈስህ ይምራኝ፣ መዝ. 143:10ሐ

ለ. ሦስት ዓይነት አካላት አሉ፣ በዚህ መዝሙር ላይ ባሕርያቸው የተሳለ።
1. ያህዌ
   ሀ. ታማኝ፣ መዝ. 143 1ሐ
   ለ. ጻድቅ፣ መዝ. 143:1ሐ፣11ለ
   ሐ. መሐሪ፣ መዝ. 143:8ሀ፣12ሀ
   መ. መዝ. 143:10ሐ እና 11ሀ ላይ ትይዩው ሐረጎች (ማለትም፣ "ቅዱሱ መንፈስህ" እና "ስምህ") ደግሞ የያህዌ ባሕርይ ነው
2. መዝሙረኛው
   ሀ. ነፍሱ አልቃለች፣ መዝ. 143፡4ሀ
   ለ. ነፍሱ ደንግጣለች፣ መዝ. 143፡4ለ

ሐ. የእግዚአብሔርን የቀድሞ ሥራዎች ያስታውሳል፣ መዝ. 143፡5
መ. እግዚአብሔርን ይናፍቃል፣ መዝ. 143፡6
ሠ. ነፍሱ ዝላለች፣ መዝ. 143፡7ሀ
ረ. በእግዚአብሔር ይታመናል፣ መዝ. 143፡8ለ
ሰ. ነፍሱን ወደ እግዚአብሔር ያነሣል፣ መዝ. 143፡8መ
ሸ. በእግዚአብሔር ተማጽኗል፣ መዝ. 143፡9ለ
ቀ. ያህዌ አምላኩ ነው፣ መዝ. 143፡10ለ

3. ጠላት
ሀ. መዝሙረኛውን ያሳድዳል፣ መዝ. 143፡3ሀ
ለ. ሕይወቱን አድቅቋታል፣ መዝ. 143፡3ሀ
ሐ. በጨለማ ስፍራ እንዲኖር አድርጎታል፣ መዝ. 143፡3ሐ
መ. መዝሙረኛውን አጎሳቁሏል፣ መዝ. 143፡12ለ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡143፡1-4**

**[1]አቤቱ፥ ጸሎቴን ስማ**
**በእውነትህ ልመናዬን አድምጥ፥**
**በጽድቅህም መልስልኝ።**
**[2]ሕያው ሁሉ በፊትህ ጻድቅ አይደለምና**
**ከባሪያህ ጋር ወደ ፍርድ አትግባ።**
**[3]ጠላትህ ነፍሴን አሳድዶአታል፥**
**ሕይወቴንም በምድር ውስጥ አጐስቍሎአታል**
**ቀድሞ እንደ ሞተ ሰው በጨለማ አኑሮኛል።**
**[4]ነፍሴ በውስጤ አለቀችብኝ፥**
**ልቤም በውስጤ ደነገጠብኝ።**

**143፡1 "ታማኝነት"** ይህ ስም (ቢዲቢ 53) የመጣው ከግሥ ነው (ቢዲቢ 52) "ማመን"ን፣ "እምነት"ን፣ "መታመን"ን፣ እና "ታማኝነት"ን ከሚገልጽ ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት፣ እና ታማኝነት በብኪ።
የተለየ ቃል (ቢዲቢ 105፣ ኬቢ 120) መዝ. 143:8ለ ላይ "መታመን" ማለት ነው

▣ **"ጻድቅ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ።
የያህዌ ባሕርይ እንዴት እንደተገለጸ ተገንዘብ፣ ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት ተመልከት፣ ለ. 1።

**143፡2** እግዚአብሔር ኃጢአትን ቢቆጥር፣ ማን ይቆማል? ሰዎች ሁሉ በዘፍጥረት 3 ውድቀት ተጎድተዋል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ውድቀት እና መዝ. 130፡3-4 ላይ ያለውን ማስታወሻ)።
አንዳንድ ራቢዎች የሚያስረግጡት ኃጢአት ዘፍጥረት 3 ላይ መጀመሩን ነገር ግን ባብዛኛው ዘፍጥረት 6 ላይ መሆኑን ነው። ራቢዎች የሚያስረግጡት የሰዎች ምርጫዎች የክፉ ምንጭ መሆናቸውን ነው (ማለትም፣ ሁለቱ *የትዛርስ*)። ጳውሎስ የሚያስረግጠው ዘፍጥረት 3 ምንጭ እንደሆነ ነው (ሮሜ. 1፡18-3፡20፤3፡23፤11፡32፤Gal. 3፡22)። ውጤቱ ተመሳሳይ ነው፣ ሰዎች ዓመጸኞች እንደሆኑና ምሕረት እንደሚያስፈልጋቸው (1 መን. 8፡46፤ኢዮብ 4፡17፤9፡2፤25፡4፤መዝ. 130፡3-4፤ምሳ. 20፡9፤መክ. 7፡20፤ኢሳ. 53፡6፤ሮሜ. 5፡12-21)!

**143፡2ለ** ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 1151) ይህ ስንኝ ቅኔ መሆኑን ይገልጻል፣ በLXX እንደ ተተረጎመው፣ በጳውሎስም ሮሜ. 3፡20 እና ገላ. 2፡16 ላይ እንደተጠቀሰው።

**143፡3-4** እነዚህ ቁጥሮች በቅኔአዊ ቋንቋ የተሳዳጁን መዝሙረኛ ስሜቶች ይገልጻሉ። ምናባዊ ምስያው ከዕብራይስጡ ጽንሰ-ሐሳብ ከሲኦል ጋር ይዛመዳል (ኢዮብ 10፡21፤መዝ. 88፡5-6፤ ሰቆ. 3፡6)።
ነገር ግን ጽንፈኛ ለውጡን ተገንዘቡ፣ መዝ. 143፡5 ላይ የመጣውን፣ መዝሙረኛው የያህዌን የቀድሞ አስደናቂ፣ አስገራሚ ሥራዎችን ሲያንጸባርቅ (ማለትም፣ ፍጥረት፣ የአባቶች መጠራት፣ የእስራኤል ሕዝብ መሆንና የተስፋይቱን ምድር መሙላት፣ ወዘተ)።

**143፡3 "ጠላት"** ይህንን እይ (*ቃል አንቀጽ*) ከነጠላ ቁጥር ግሦች ጋር መያያዙን። ሁለት የተሻሉ አማራጮች አሉ።
1. የጥቅል ቃል (የብዙ መዝ. 143፡9፣12)
2. አንድ ዋነኛ ጠላት
3. የ"ሞት፣" የ"ጥልቁ፣" የ"ሲኦል" መጣቀሻ

**143፡4 "መንፈስ... ልብ"** እነዚህ ሁለቱም ግለሰቡን ነው የሚጠቅሱት። የመጀመሪያው ሐረግ የመዝ. 142፡39 ድጋሚ ነው፣ እዚያ ያለውን ማስታወሻ ተመልከት።
ተመሳሳይ ሐሳብ መዝ. 143፡7ሀ ላይ ተደግሟል።
ለ "መንፈስ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ መንፈስ በመጽሐፍ ቅዱስ።
ለ "ልብ" ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ልብ።

▣ **"አለቀ"** ይህ በጥሬው "መዛል" ነው
(ቢዲቢ 742፣ ኬቢ 814፣ *Hithpael ያልተጠናቀቀ* ከ*ዋው ጋር፣ መዝ*. 142:3*ሀ*)። ይህ *ግሥ* ጥቅም ላይ የዋለው
1. ከመንፈስ (*ሩሕ*) – *መዝ*. 77:3፤142:3፤143:4
2. ከልብ (*ልብ*) – *መዝ*. 61:2፤143:4
3. ነፍስ (*ኔፌሽ*) – *መዝ*. 107:5

***መዝሙር :143፡5-6***
[5]***የቀድሞውን ዘመን አሰብሁ፥***
***ሥራህንም ሁሉ አሰላሰልሁ***
***የእጅህንም ሥራ ተመለከትሁ።***
[6]***እጆቼን ወደ አንተ ዘረጋሁ***
***ነፍሴም እንደ ምድረ በዳ አንተን ተጠማች።*** ***ሴላህ።***

**143፡5-6** ይህ *የመዝሙረኛውን* ድርጊቶች ይገልጻል።
1. እሱ የእግዚአብሔርን የቀድሞ ድንቅ የማዳን *ሥራዎች* ያስታውሳል፣ *መዝ*. 143፡5*ሀ*
2. እሱ የእግዚአብሔርን *ሥራዎች* ማሰላሰሉን ቀጥሏል፣ *መዝ*. 143:5*ለ*፣ ዝከ. 105:2
3. እሱ ያንጸባርቃል/ያሰላስላል (*መዝ*. 77:12፤145:5) የእግዚአብሔርን ፍጥረት *መዝ*. 143:5*ሐ*፣ *መዝ*. 8:6፤102:25
4. ወደ እግዚአብሔር ይለምናል፣ *መዝ*. 143:6*ሀ*
5. ነፍሱ እግዚአብሔርን ትናፍቃለች፣ *መዝ*. 143:6*ለ*፣ *መዝ*. 42:2፤63:1

እነዚህ የታማኝ ተከታይ ሐሳብ ትኩረቶች ናቸው። እኛ የምናስበውን ነን። ጸሎታችንና ድርጊታችን የእያንዳንዱን ሰው እውነተኛ ተፈጥሮ ይገልጻል።

**143:5 "የቀድሞ ዘመን"** ይህ ስም (ቢዲቢ 869) ሊል የሚችለው "የጥንት" ወይም "የድሮ" ነው (ዘዳ. 33:27፤ምሳ. 8:22-23፤ሚክያስ 5:2)። *ሥሩ* ዘወትር የሚጠቅሰው "ምስራቅ" ወይም "ቀድሞ" ነው (ኒዶቲ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 869-871)።

**143:6 "እጆቼን ወደ አንተ እዘረጋለሁ"** ማስታወሻ ተመልከት *መዝ*. 141:2*ለ* ላይ።

▣ **"ነፍስ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል ኔፊሽ ነው። ማስታወሻ ተመልከት ዘፍ. 35፡18 ላይ፣ በድረ ገጽ ቀጥታ መስመር።

▣ **"ነፍሴም እንደ ምድረ በዳ አንተን ተጠማች።"** መዝሙረኛው ከያህዌ ጋር ግላዊ ግንኙነትን ናፍቋል/ተጠምቷል (*መዝ*. 143:7*ለ*፤*መዝ*. 42:2፤ 63:1፤84:2)። ይህ የዘፍ. 1:26-27 ግብ ነው። እሱም የፍጥረት ዓላማ ነው!
የያህዌን ድርጊቶች ማስታወስ እና አምልኮ በወቅቱ ሁኔታ ላይ ተስፋን እንደሚሰጥ ተገንዘብ!

▣ **"ሴላህ"** ማስታወሻ ተመልከት *መዝ*. 3፡2 ድረ ገጽ ቀጥታ መስመር ላይ።

***መዝሙር :143፡7-9***
[7]***አቤቱ፥ ፈጥነህ ስማኝ ነፍሴ አልቃለች***
***ፊትህን ከኔ አትመልስ፥***
***ወደ ጉድጓድም እንደሚወርዱ አልሁን።***
[8]***አንተን ታምኘለሁና***
***በማለዳ ምሕረትህን አሰማኝ***
***አቤቱ፥ ነፍሴን ወደ አንተ አንሥቻለሁና***
***የምሄድበትን መንገድ አስታውቀኝ።***
[9]***አቤቱ፥ ወደ አንተ ተማፅኛለሁና***
***ከጠላቶቼ አድነኝ።***

**143፡7 "ነፍሴ አልቃለች"** *ግሥ* (ቢዲቢ 477፣ ኬቢ 476፣ *ቃል* የተጠናቀቀ) ፍችው "መጠናቀቅ" ወይም "መፈጸም" ማለት ነው። እሱም ለሰው ጥቅም ላይ የዋለው
1. ኢዮብ 33:21፣ *ሥጋዬ* አለቀ
2. *መዝ*. 71:9፣ *ኃይሌ* አለቀ
3. *መዝ*. 73:26፣ *ሥጋዬ*ና ልቤ አለቀ
4. ምሳ. 5:11፣ *ሥጋዬ*ና አካሌ አለቀ

*መዝሙረኛው* እንደሚሞትና ወደ ሶኦል እንደሚወርድ ተሰምቶታል (ማለትም፣ ጉድጓድ፣ *መዝ*. 143:7*ሐ*)።

▣ **"ፊትህን ከእኔ አትመልስ"** ይህ ፈሊጣዊ፣ ሰውኛ (አንትሮፖሞርፊክ) ቋንቋ (1) እግዚአብሔር ዝም ሲልና ለመዝሙረኛው ጸሎት ምላሽ ሳይሰጥ ወይም (2) እግዚአብሔር *መዝሙረኛውን* ሳይቀበል ነው፤ ዐውደ-ጽሑፍ ወይም ትይዩነት ብቻ ሊወስነው ይችላል (*መዝ*. 10:11፤13:1፤27:9፤30:7፤ 51:9፤69:17፤88:14፤102:2)። እሱም የተስፋ-ቢስነትን ረዳት የለሽነትን ይገልጻል (*መዝ*. 142:4)።

**143:8ሐ *"የምሄድበትን መንገድ አስታውቀኝ"*** ይህ ግሥ (ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ *ሂፊል ተተኳሪ*) መሠረታዊ ፍቾው "ማወቅ" ነው። አአመመቅ የሚተረጉመው እንደ

1. ማሳወቅ – 1 ዜና. 17:19፤ኢዮብ 26:3፤መዝ. 89:1፤98:2፤106:8፤145:12፤ኢሳ. 64:1፤ዕን. 3:2
2. ማስተማር – ዘጸ. 18:20፤ኤር. 31:19፤እና እዚህ

"መራመድ" ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው ለየዕለቱ ሕይወት ዘይቤ ነው (ማለትም፣ መዝ. 1:1፤ምሳ. 1:15፤4:14፤ኢሳ. 48:17፤ኤር. 42:3፤ አኪ. ላይ ደግሞ፣ ማለትም፣ ሮሜ. 14:15፤ኤፌ. 4:1፣17፤5:2፣15)።

**143:8መ *"ነፍሴን ወደ አንተ አነሣለሁ"*** ይህ ምናባዊ ሊሆን ይችላል፣ ሦስት ጊዜ ብቻ ከያህዌ ጋር በተያያዘ ጥቅም ላይ ውሏል (መዝ. 25:1፤86:4)

1. ጸሎት (ማለትም፣ እጆቼን/ክንዶቼን አነሣለሁ)
2. መሥዋዕት (ማለትም፣ የመወዝወዝ መሥዋዕት ወይም የቀንዶቹ ምናባዊ ምስያነት፣ የመሥዋዕቱ መሠዊያ)

**143:9**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | ***"በአንተ ተማጽኛለሁ"*** |
| **አኪጀቅ** | ***"በአንተ ተጠግቻለሁ"*** |
| **አኢመቅ** | ***"በአንተ መጠጊያ ስላገኘሁ"*** |
| **ጀፒኤስአኤ** | ***"በአንተ ዘንድ መከለያ እሻለሁ"*** |
| **የተእመቅ** | ***"በአንተ መጠጊያ እሻለሁ"*** |
| **LXX፣ ቯልጌት** | ***"ወደ አንተ እሸሻለሁ"*** |

አንቀጹ (ቢዲቢ 491፣ ኬቢ 487፣ *ፒል አንቀጽ*) መሠረታዊ ፍቾው "መሸፈን" ወይም "መደበቅ" ነው። እሱም እጅግ የተለመደ ሥር ነው፣ በብኪ።

ኤቢ (ገጽ 325) ይሄንን የቅኔ ስንኝ የሚተረጉመው "አምላኬ (ኤል)፣ በእውነት ተሸፍኛለሁ" በሚል ነው። ዳሆድ እሱን የሚያያይዘው ሲኦልን ለመጥቀስ ነው፣ ኢዮብ 22:11ን በመጠቀም።

ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 1153) ሁለት የዕብራይስጥ ኤምኤስኤስ ይጠቅሳል፣ እሱም ኤምቲን በተለየ መልኩ የሚተረጉም።

1. "በአንተ ዘንድ መጠጊያ እሻለሁ"
2. "ወደ አንተ እሸሻለሁ"

## መዝሙር ፡143፡10-12

**10 አንተ አምላኬ ነህና**
**ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ**
**ቅዱስ መንፈስህም በጽድቅ ምድር ይምራኝ።**
**11 አቤቱ፥ ስለ ስምህ ሕያው አድርገኝ**
**በጽድቅህም ነፍሴን ከመከራዋ አውጣት።**
**12 በምሕረትህ ጠላቶቼን ደምስሳቸው፥**
**እኔ ባሪያህ ነኝና**
**ነፍሴን የሚያስጨንቁአትን ሁሉ አጥፋቸው።**

**143:10 *"ፈቃድህን ለማድረግ አስተምረኝ"*** ይህ የተለየ ቃል ነው (ቢዲቢ 540፣ ኬቢ 531፣ ዘዳ. 4:1፤6:1፤20:18፤ ኤር. 12:16) ከ"ማስተማር" የመዝ. 143:8ሐ። ያህዌ ፈቃዱን ሊያስተምረን ይፈልጋል፣ ታማኝ ተከታዮቹ ለጠፋው ዓለም ማሳያ መሆን ይችሉ ዘንድ!

ደግሞም ሉዓላዊው አምላክ ፍቃዱን እንደሚገልጥ ተመልከቱ፣ ሰዎችም ለማድረግ መወሰን እንደሚኖርባቸው (እናም ማድረጋቸውን መቀጠል) በዚህ ራዕይ ላይ። ኪዳኑ ሁለቱንም እግዚአብሔርንና ሰዎችን ያካትታል!

**▣**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | ***"ቅዱሱ መንፈስህ"*** |
| **አኪጀቅ** | ***"መንፈስህ መልካም ነው"*** |
| **አየተመቅ፣ LXX** | ***"ቅዱሱ መንፈስህ"*** |
| **አኢመቅ** | ***"ለጋሱ መንፈስህ"*** |
| **ጀፒኤስአኤ፣ የተእመቅ** | ***"ባለ ጸጋው መንፈስህ"*** |
| **ፔሺታ** | ***"መልካሙ መንፈስህ"*** |

ከእንግሊዝኛ ትርጉሞች ግልጽ እንደሆነው ሁለት ሥነ-መለኮታዊ ጉዳዮች አሉ።

1. "መንፈስ"ን እንዴት ማየት እንደሚቻል
   ሀ. የእግዚአብሔር ወኪል ምናባዊ ምስያ (ማለትም፣ ዘፍ. 1:2፤ዘኍ. 11:17፣25፣29፤መዝ. 139:7፤ሐጌ 2:5)
   ለ. የእግዚአብሔር የራሱ ባሕርይ (መዝ. 51:11፤ኢሳ. 63:10-11)
2. የ "መልካም" መግለጫ (ቢዲቢ 373 III)፣ ይኸውም የተለመደ ግሥ ነው፣ በሰፊ የፍች መስክ፤ አጠቃላይ ስሜቱም
   ሀ. "የሚያስደስት፣" "መልካም" (ግሥ)
   ለ. "አስደሳች፣" "ስምም፣" "መልካም" (ቅጽል)
   ሐ. "መልካም ነገር፣" "መልካምነት" (ተባዕታይ ስም)
   መ. "ማለፊያ፣" "ጠቀሜታ፣" "መልካም ነገር" (አንስታይ ጾታ)

ለ ቁ. 1 እባክዎትን ልዩ ርዕስ ተመልከቱ፡ የመንፈስ ቅዱስ አካላዊነት እና ልዩ ርዕስ፡ ሥላሴ።

▣ **"የተስተካከለ ምድር"** ብኪ የመንገድ/ፍኖት/ጎዳናን ምናባዊ ምስያ የአንዱን ሕይወት ለመግለጽ ይጠቀማል (መዝ. 5:8፤26:12፤27:11)።

1. መልካም/የጽድቅ ሕይወት የሚባለው
   ሀ. የለዘበ
   ለ. የተስተካከለ
   ሐ. ማሰናከያ የሌለበት
   መ. ቀና
2. የኃጢአተኛ ሕይወት የሚባለው
   ሀ. ጠማማ
   ለ. ያልተስተካከለ
   ሐ. ማሰናከያ ያለው
   መ. የሚያንሸራትት

**143፡11-12** መዝሙረኛው ጥያቄውን የመሠረተው፣ በራሱ ሥራ ላይ አይደለም (መዝ. 143፡2)፣ ነገር ግን

1. በእግዚአብሔር መልካም ስም ላይ፣ መዝ. 143፡11ሀ
2. በእግዚአብሔር ጽድቅ ላይ፣ መዝ. 143፡11ለ
3. የእግዚአብሔር ምሕረት፣ መዝ. 143፡12ሀ

**143፡11 "ስለ ስምህ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣** | |
| **አእቅ፣ የተእመቅ** | **"ሕያው አድርገኝ"** |
| **አየተመቅ፣ ጄፒኤስአኤ** | **"ሕይወቴን ጠብቅ"** |
| **አኢመቅ** | **"ሕይወትን ስጠኝ"** |
| **LXX** | **"ሕይወትን ስጠኝ"** |

ግሡ (ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 309፣ ፒል ያልተጠናቀቀ) የወል ቃል "ሕይወት" ነው (ስም)፣ "መኖር" (ግሥ)፣ "በሕይወት፣" ወይም "መኖር" (ቅጽል)። ይህ ፔል ሥር በመዝሙር  ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል (መዝ. 80:18፤85:6፤119:25፣37፣ 40፣50፣88፣93፣107፣149፣154፣156፣ 159)። እሱም ዘወትር ትይዩ ነው፣ ከ ቢዲቢ 996፣ ኬቢ 1427፣ መዝ. 80:3፣17፣19 ጋር። ሊያመለክት የሚችለውም

1. ሕጋዊ ሕይወት
2. መንፈሳዊ ሕይወት

**143፡12 "ባርያህ"** ይህ ፍችው የሚሆነው

1. ታማኝ ተከታይ
2. የመሪዎች የክብር ስም
   ሀ. ሙሴ
   ለ. ኢያሱ
   ሐ. ዳዊት (ማለትም፣ የይሁዳ ነገሥታት)
   መ. መሲሕ/እስራኤል (ማለትም፣ የአገልጋይ መዝሙራት፣ የኢሳይያስ 41-53)

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ሰዎች ሁሉ ኃጢአተኛ ሆነው ሳለ፣ መዝሙረኛው እግዚአብሔር እንዲሰማውና እንዲረዳው የሚጠይቀው ምንን መሠረት አድርጎ ነው?
2. "ጠላት" ማነው?
3. "የጨለማ ስፍራዎች" መዝ. 143፡3 ላይ የሚለውን ግለጽ።
4. ያህዌ "ፊቱን መሸፈኑ" አንድምታው ምንድነው?
5. መዝ. 143፡10 መንፈስ ቅዱስን የሚጠቅስ ነውን?
6. "ባርያ" የሚለውን አብራራ።

# መዝሙር 144
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ጸሎት ለመታደግና ለብልጽግና<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር | ዝማሬ ለጌታ ሕዝቡን ለሚጠብቀውና ለሚያበለጽገው | የንጉሥ ጸሎት ለመዳን | ንጉሥ እግዚአብሔርን ስለ ድል ሲያመሰግን | ውዳሴ ስለ ጦርነትና ድል |
| 144:1-4 | 144:1-2 | 144:1-2 | 144:1-2 | 144:1-2 |
| | 144:3-4 | 144:3-4 | 144:3-4 | 144:3-4 |
| 144:5-8 | 144:5-8 | 144:5-8 | 144:5-8 | 144:5-6 |
| | | | | 144:7-8 |
| 144:9-11 | 144:9-10 | 144:9-11 | 144:9-11 | 144:9-10ለ |
| | | | | 144:10ሐ-11 |
| | 144:11-15 | | | |
| 144:12-15 | | 144:12-14 | 144:12-14 | 144:12 |
| | | | | 144:13 |
| | | | | 144:14 |
| | | 144:15 | 144:15 | 144:15 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡144፡1-4**

**1እግዚአብሔር አምላኬ ይባረክ፥**
**ለእጆቼ ሰልፍን፥**
**ለጣቶቼም ዘመቻን የሚያስተምር**
**2መሓሪዬና መሸሸጊያዬ፥**
**መጠጊያዬና መድኃኒቴ**
**ረዳቴና መታመኛዬም**
**ሕዝቤንም ከእኔ በታች የሚያስገዛልኝ።**
**3አቤቱ፥ እርሱን ታውቀው ዘንድ ሰው ምንድር ነው?**
**ታስብለት ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው?**
**4ሰው ከንቱን ነገር ይመስላል**
**ዘመኑ እንደ ጥላ ያልፋል።**

**144፡1-4** ይህ አንዳ በርካታ ወታደራዊ ጠቃሾችን ይጠቀማል። ይህ በርግጥ ንጉሣዊ መዝሙር ነው። ያህዌ በሕዝቡ ጎን ይሠራል፣ ደኅንነታቸውን ለማረጋገጥ፣ ምክንያቱም ሁለንተናዊ የመዋጀት ዕቅድ ስላለው፣ ብሔረ-እስራኤልን በማካተት (የአብርሃም ዘሮች)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

መዝሙር 134፡3-4 ያስገርማል፣ ትኩረቱ ከእስራኤል ወደ ሰዎች ሁሉ በመዞሩ።

1. እነርሱ የእግዚአብሔር የተለየ ክብካቤ የሚመለከታቸው ናቸው (መዝ. 8፡4) በእርሱ መልክና አምሳል ስለ ተፈጠሩ (ዘፍ. 1፡26-27)
2. ሆኖም፣ በዘፍጥረት 3 ምክንያት እነርሱ ደካማና የተወሰኑ ናቸው (መዝ. 90:5፤103:15፤104:14፤ኢሳ. 40:6-8፤1 ጴጥ. 1:24)

**144:1 "ይባረክ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ባርኮት (ብኪ)።

▣ **"ዓለቴ"** ይህ (ቢዲቢ 849) ተደጋጋሚ መጠሪያ ነው፣ ለእስራኤል አምላክ። ማስታወሻ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ተመልከት፣ ዘዳ. 32:4 ዝና መዝ. 18:1-3 ላይ። ሁሉም ነገር ይቀየራል እግዚአብሔር ብቻ እንጂ። እሱ የማይወድቅ መልኅቅ ነው፣ ምሽግ ነው የማይሰበር። ብርቱ፣ ስሜታዊ በቅደም ተከተል የተቀመጡትን ገላጭ ስሞች መዝ. 18፡2 ላይ ተመልከት!

▣ **"ለእጆቼ ሰልፍን የሚያስተምር"** በርግጥ ጽሑፋዊ ግንኙነት በመዝሙር 18 እና መዝሙር 144 መካከል አለ። ትይዩዎቹን ተመልከት።

1. መዝ. 144:1 – መዝ. 18:2፣34፣46
2. መዝ. 144:2 – መዝ. 18:2፣47
3. መዝ. 144:3 – መዝ. 18:4
4. መዝ. 144:5 – መዝ. 18:9
5. መዝ. 144:6 – መዝ. 18:14
6. መዝ. 144:7 – መዝ. 18:16-17፣44
7. መዝs. 144:10 – መዝ. 18:50
8. መዝ. 144:11 – መዝ. 18:44

**144:2 "መሐሪዬ"** ያህዌ በኪዳን ቁርጠኝነቱ የታመነ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት (ሄስድ)።

በርካታ ሰዋዊ ተውላጠ ስሞቹን ተመልከት፣ አአመመቅ መዝ. 144፡1-2 ላይ (ስድስት)። መዝሙረኛው እግዚአብሔርን ያውቃል፣ ይታመናልም።

▣

**አአመመቅ፣ አኪጀቅ፣**

**LXX** **"ሕዝቤን ከበታቼ የሚያስገዛልኝ"**

**አየተመቅ፣ አእቅ፣**

**ታርጉምስ፣ ፔሺታ፣**

**ቫልጌት** **"ሕዝብን ከበታቼ የሚያስገዛልኝ"**

**አኢመቅ** **"ሕዝቦችን ከበታቼ የሚያስገዛልኝ"**

ልዩነቱ የመጨረሻው *ሜም* (የዕብራይስጥ ፊደል) ብቻ ነው። የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 436) "ሕዝቤ" ለሚለው "ለ" ደረጃ ይሰጠዋል (መጠነኛ ጥርጣሬ)። ይህ የቅኔ ስንኝ አንድም

1. የንጉሡን ሥልጣን የሚያስረግጥ ነው፣ በኪዳን ሕዝቡ ላይ ያለውን (ማለትም፣ እሱ ከያህዌ በታች ያለ እረኛ ነው)
2. የእስራኤልን ድል አድራጊነት ያስረግጣል፣ በያህዌ ኃይል፣ በጣዖት አምላኪ ሕዝቦች ላይ

የዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 437) "በበታቼ" ለሚለው "ሀ" ደረጃ ይሰጠዋል፣ (እጅግ ከፍተኛ ይሁንታ)። ይህ ትክክለኛው ጽሑፍ ከሆነ፣ እንግዲያውስ ከላይ ያለው አማራጭ ቁ. 1 ትክክለኛው ሐረግ ነው።

**144፡3** ተመሳሳዩን ትይዩነት ተገንዘብ።

1. "ሰው" — አዳም (ቢዲቢ 9)
2. "የሰው ልጅ" — "ቤን ኢኖሽ" (ቢዲቢ 60)

በትይዩ መዝሙር 8 ላይ የዕብራይስጥ ቃላት "ለሰው" ተገልብጠዋል፣ ነገር ግን ሐሳቡ አንድ ነው። እነዚህ ቃላት የሚናገሩት ስለ ሰብዓዊ ፍጡር ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የሰው ልጅ (ከዳን. 7፡13)።

▣ **"ታውቀው ዘንድ"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል "ማወቅ" ነው (ቢዲቢ 393፣ ኬቢ 390፣ *ቃል* ያልተጠናቀቀ ከ*ዋው ጋር*)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማወቅ።

**144:4** ይህ ቁጥር የሰውን ልጅ ውስን መሆን አጉልቶ ያሳያል (ኢዮብ 8:9፤14:2፤መዝ. 39:5-6፤102:11፤109:23፤መክ. 6:12፤8:12) እናም ምንም እንኳ ተለይቶ ባይቀመጥም፣ የእግዚአብሔር ዘላለማዊነት በጉልህ ተመልክቷል።

## መዝሙር ፡144፡5-8

**5 አቤቱ፥ ሰማዮችህን ዝቅ ዝቅ አድርጋቸው ውረድም**
**ተራሮችን ዳስሳቸው ይጢሱም።**
**6 መብረቆችህን ብልጭ አድርጋቸው በትናቸውም**
**ፍላጾችህን ላካቸው አስደንግጣቸውም።**
**7-8 እጅህን ከአርያም ላክ**

**አድነኝም ከብዙ ውኆች፥**
**አፋቸውም ምናምንን ከሚናገር፥**
**ቀኛቸው የሐሰት ቀኝ ከሆነ፥**
**ከባዕድ ልጆች እጅ አስጥለኝ።**

**144፡5-8** ይህ አንጓ ተለጣጣቂ የሆኑ የጸሎት ጥያቄዎች ነው። እሱም ከመዝ. 144፡1-4 አኳያ ያስደንቃል። መዝሙረኛው በመጀመሪያው አንጓ ላይ የያህዌን ኃይልና መገኘት ያስረግጣል፤ ነገር ግን በዚህኛው ላይ ማዳኑን ይለምናል።

በተተኳሪ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉትን ተተኳሪዎችና ያልተጠናቀቁትን ተመልከት።

1. ዝቅ ማድረግ፣ መዝ. 144:5 ("መጉበጥ") – ቢዲቢ 639፣ ኬቢ 692፣ ሂፊል ተተኳሪ
2. ውረድ፣ መዝ. 144:5 – ቢዲቢ 432፣ ኬቢ 434፣ ቃል ያልተጠናቀቀ ግን በተተኳሪያዊ የጸሎት ጥያቄ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
3. ዳስሳቸው፣ መዝ. 144:5 – ቢዲቢ 619፣ ኬቢ 668፣ ቃል ተተኳሪ፣ መዝ. 104:32
4. ብልጭ አድርጋቸው፣ መዝ. 144:6 – ቢዲቢ 140፣ ኬቢ 162፣ ቃል ተተኳሪ
5. በትናቸው (ማለትም፣ ፍላጾችን በባዕድ ወራሪዎች ላይ)፣ መዝ. 144:6 – ቢዲቢ 806፣ ኬቢ 918፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ የጸሎት ጥያቄ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
6. ላካቸው፣ መዝ. 144:6 – ቢዲቢ 1018፣ ኬቢ 1511፣ ቃል ተተኳሪ
7. አስደንግጣቸው፣ መዝ. 144:6 – ቢዲቢ 243፣ ኬቢ 251፣ ቃል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ የጸሎት ጥያቄ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
8. ላክ፣ መዝ. 144:7 – ከቁ. 6 ጋር ተመሳሳይ
9. አድን ( ከፈት፣" መዝ. 144:11)፣ መዝ. 144:7 – ቢዲቢ 822፣ ኬቢ 953፣ ቃል ተተኳሪ
10. አድነኝም፣ መዝ. 144:7 – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ ሂፊል ተተኳሪ

**144፡5-7** እነዚህ ቁጥሮች "የቅዱስ ጦርነት"ን ምናባዊ ምስያ ይጠቀማሉ፣ የያህዌን መገኘትና ኃይል ለመጠየቅ፣ በጦርነት ላይ። እሱ አንድም

1. የእስራኤልን ወታደሮች አሠልጥኖ ኃይል ያስታጥቃቸዋል (መዝ. 144፡1)
2. በእስራኤል በኩል ሆኖ ተዋግቷል፣ በኢያሱ አማካኝነት ከነአን ድል እንደተደረገው (መዝ. 144፡6)

**144፡6**

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | **"አስደንግጣቸው"** |
| **አኪጀቅ** | **"አጥፋቸው"** |
| **አየተመቅ፣ አኢመቅ** | **"አሸንፋቸው"** |
| **አእቅ** | **"አባርራቸው"** |
| **LXX** | **"ወደ ድንጋጤ ጣላቸው"** |

ሁለት ታሳቢ የዕብራይስጥ ሥሮች አሉ።

1. ◻מ፣ ቢዲቢ 243፣ ኬቢ 251፣ "ማባረር፣" 2 ሳሙ. 22:15፤መዝs. 18:14
2. ◻ה፣ ኬቢ 242፣ "መደንገጥ፣" ይኸኛው "ቅዱስ ጦርነት" የሚል ፍች አለው፣ ኢያ. 10:10፤ መሳ. 4:15፤1 ሳሙ. 7:10፤2 ዜና. 15:6

**144:7** "ብዙ ውኆች" "የባዕዳን እጅ" ከሚለው ጋር ትይዩ መሆኑን ተገንዘብ። ምስያው

1. ከፍጥረት ሁከት፣ ኢዮብ 41:1-11፤መዝ. 74:12-17፤ኢሳ. 51:9-10 ላይ ነው፤ልዩ ርዕስ ተመልከት: ውኆች
2. ወረራ፣ መዝ. 18:16-17፤ኢሳ. 17:12-14፤28:2፤ኤር. 51:34
3. ሞት፣ መዝ. 18:4-6

**144፡8** ባዕዳን (ቢዲቢ 648) ባሕርያቸው እንደሚዋሹ ነው። የአንዱ ቃላት ልቡን ይገልጻል። ይህም የሚያመለክተው ዓለም አቀፋዊ ስምምነቶችን (ቃል -ኪዳኖችን) ወይም የፍርድ ቤት ምስክርነትን ነው፣ በመሐላ ሥር (ዘፍ. 14:22፤ዘዳ. 32:40፤መዝ. 106:26፤ኢሳ. 44:20)። እግዚአብሔር ለቃሉ እውነት ነው (መዝ. 144:2ሀ)፣ ነገር ግን ጣዖት አምላኪዎችና አንዳንድ እስራኤላውያን እውነተኞች አይደሉም! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የሰው ንግግር።

## መዝሙር ፡144፡9-11

**[9]አቤቱ፥ አዲስ ቅኔ እቀኝልሃለሁ**
**አሥር አውታር ባለው በገና እዘምርልሃለሁ።**
**[10]ለነገሥታት መድኃኒትን የሚሰጥ፥**
**ባሪያውን ዳዊትን ከክፉ ሰይፍ የሚያድነው እርሱ ነው።**
**[11]አድነኝ፥ አፋቸውም ምናምንን ከሚናገር፥**
**ቀኛቸውም የሐሰት ቀኝ ከሆነ፥**
**ከባዕድ ልጆች እጅ አስጥለኝ።**

**144፡9-11** ይህ አንጓ ሦስት አጽንዖቶች አሉት።

1. መዝሙረኛው ለማድረግ ቃል የገባው
   ሀ. ለእግዚአብሔር አዲስ ዝማሬ እዘምራለሁ መዝ. 144:9ሀ – ቢዲቢ 1010፣ ኬቢ 1479፣ ቃል ተጓዳኝ
   ለ. ለእግዚአብሔር ምስጋና እዘምራለሁ፣ መዝ. 144:9ለ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ፒል ተጓዳኝ
2. የያህዌ የቀድሞ የማዳን ሥራ

ሀ. እሱ የእስራኤልን ነገሥታት አድናል፣ መዝ. 144፡10ሀ
ለ. ዳዊትን አድኗል፣ መዝ. 144፡10ለ (የዳዊትን ዝርያ ነገሥታትን ይሆናል)
3. የመዝሙረኛው ጸሎት የተመሠረተው በያህዌ የቀድሞ ሥራዎች ላይ ነው
ሀ. አድነኝ፣ 144፡11ሀ – ቢዲቢ 822፣ ኬቢ 963፣ ቃል ተተኳሪ
ለ. አድነኝ፣ መዝ. 144፡11ሀ – ቢዲቢ 664፣ ኬቢ 717፣ ሂፊል ተተኳሪ
ትይዩውን ተገንዘብ፣ በመዝ. 144፡7-8 እና 144፡11 መካከል ያለውን።

**144፡10 "ከክፉ ሰይፍ"** ይህ ያልተለመደ ባሕርይ አሳሳል ነው። በርካታ ትርጉሞች ሐረጉን የሚያስቀምጡት በቀጣዩ የቅኔ ስንኝ (መስመር) ላይ ነው (ማለትም፣ አየተመቅ፣ አእቅ፣ አኢመቅ)። ሌሎች ትርጉሞችም አላቸው
1. የተእመቅ– "ጨካኝ ሰይፍ"
2. ጀፒኤስኦኤ – "ገዳይ ሰይፍ"
3. ኪጀቅ፣ ፔሺታ – "ጎጂ ሰይፍ"
4. ኤቢ – "ከክፉው ሰይፍ"
5. አአመቅ – "ክፉ ሰይፍ"

ከዐውደ-ጽሑፍ አኳያ ከ"ባዕዳን" ጋር ይዛመዳል (መዝ. 144፡7ሐ፣ 11ሀ)። አራማዊው ታርጉም (ከአስተያየት ጋር የሆነ ትርጉም) እሱን የሚተረጉመው "ከጎልያድ ክፉ ሰይፍ" በሚል ነው (ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ፣ ገጽ 1159)።

## መዝሙር ፡144፡12-15

**12 ልጆቻቸው በጕልማስነታቸው እንደ አዲስ አትክልት የሆኑ፥**
**ሴቶች ልጆቻቸውም እንደ እልፍኝ ያማሩና ያጌጡ**
**13 ዕቃ ቤቶቻቸውም የተሞሉ በየዓይነቱ ዕቃ የሚሰጡ፥**
**በጎቻቸውም ብዙ የሚወልዱ፥ በማሰማርያቸውም የሚበዙ፥**
**14 ላሞቻቸውም የሚሰቡ**
**ቅጥራቸውም መፍረሻና መውጫ የሌለው፥**
**በአደባባዮቻቸውም ዋይታ የሌለ**
**15 እንደዚህ የሚሆን ሕዝብ የተመሰገነ ነው**
**እግዚአብሔር አምላኩ የሆነ ሕዝብ ምስጉን ነው።**

**144፡12-14** ይህ አንጓ ጠባይ ያደረገው ሰባት አንቀጾችን ነው (1) እንደ ተጽዕኖዊ ጥቅም ላይ የዋሉ (2) የሐቅ መግለጫዎች (ዓረፍተ-ነገሮች)።
1. ወጣት ወንዶች ልጆች እንደ አትክልት ያደጉ፣ መዝ. 144፡12ሀ – ቢዲቢ 152፣ ኬቢ 178፣ ፖል
2. ወጣት ሴቶች ልጆች ያማሩ ("የተከረከሙ") ዓምዶች፣ መዝ. 144፡12ለ – ቢዲቢ 310፣ ኬቢ 306፣ ፖል
3. ዕቃ ቤቶቻቸው የተሞሉ፣ መዝ. 144፡13ሀ – ቢዲቢ 807፣ ኬቢ 920፣ ሂፊል
4. በጎቻቸው ብዙ የሚወልዱ፣ መዝ. 144፡13ለ – ቢዲቢ 48 II፣ ኬቢ 59፣ ሂፊል (እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው)
5. መንጎቻቸው ብዛ የሚወልዱ፣ መዝ. 144፡13ለ – ቢዲቢ 912፣ ኬቢ 1174፣ ፖል
6. ላሞቻቸው የሚወልዱ (የሚሰቡ) (በእርግዝና የሚከብዱ)፣ መዝ. 144፡14ሀ – ቢዲቢ 687፣ ኬቢ 741፣ ፖል
7. የሚወጡ (ማለትም፣፣ "የሚመላለሱ" ) ያለ ችግር፣ መዝ. 144፡14ለ – ቢዲቢ 422፣ ኬቢ 425፣ ቃል
8. የተመለከተ አንቀጽ አለ፣ መዝ. 144፡14ሐ ላይ — አአመመቅ "የሌለ" የሚል አለው፣ እሱም ከመዝ. 144፡12-14ለ ጋር የሚገጥም፣ "በአደባባያቸውም ዋይታ የሌለ"

እነዚህ ሁሉ የኪዳን መታዘዝ በረከቶች ናቸው (ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30)። የመዝ. 144፡15 የኪዳን በረከቶችን ተገንዘብ። አአመመቅ ሁለቱንም፣ መዝ. 144፡1 እና 15ን "የተባረከ" በሚል ይተረጉማቸዋል፣ ነገር ግን እነርሱ የተለዩ የዕብራይስጥ ቃላት ናቸው።
1. መዝ. 144፡1 – ቢዲቢ 138
2. መዝ. 144፡15 – ቢዲቢ 80

"ደስተኛ" ወይም "የተባረከ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 80፣ መዝ. 1፡1) ተደጋጋሚ ነው፣ የሚገልጸውም ለምን እንደተባረኩ ነው (መዝ. 32፡1-2፤34፡8፤40፡4፤84፡5፣12፤94፡12፤127፡5፤ምሳ. 3፡13፤8፡34፤28፡14)። እሱም ደግሎ ለወል ባርኮቶች ጥቅም ላይ ይውላል (መዝ. 33፡12፤89፡15፤144፡15)።

**144፡12** "አትክልት" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 642) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ነገር ግን ለተለመደው የ"አትክልት" ሥር (ግሥ) እጅግ የቀረበ ነው።
1. አትክልት (እዚህ) – נָטַע
2. አትክልት – נטע ፣ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውል

▣ **"የማዕዘን ዓምድ(ያጌጠ)"** ይህ የአልፎ አልፎ ቃል ነው፣ እዚህጋ ብቻ እና ዘካ. 9፡15 ላይ የሚገኝ።

**144፡13 "ዕቃ ቤት"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 265፣ ኬቢ 565) ደግሞ እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ (ኒዶቲ፣ ቅጽ 2፣ ገጽ 909)። አብዛኞቹ ትርጉሞች "ጎተራ" የሚል አላቸው።

**144፡14** ይህንን ቁጥር ለመመልከት ሁለት መንገዶች አሉ።
1. እሱም ከመዝ. 144፡13ለ ጋር አብሮ ይሄዳል፣ እናም ከጤናማ፣ ውጤታማ እንስሳት ሀብት ጋር ይያያዛል (ኒዶቴ፣ ቅጽ 2 ገጽ 498)።
2. እሱም ከመዝ. 144፡14ለ፣ሐ ጋር አብሮ ይሄዳል፣ እናም የከተማይቱ ቅጥር መፍረሻ እንዳይኖረው ከመጻለይ ጋር ይያያዛል፣ እሱም ለወራሪ መግቢያ እንዳይሆን።

ዩቢኤስ ማስታወሻ መጽሐፍ (ገጽ 1161) የሚያስረግጠው ከጽሑፉም ሆነ ከዐውደ-ጽሑፉ የትኛው አማራጭ የተሻለ እንደሆነ ማወቂያ መንገድ እንደሌለ ነው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ይህ መዝሙር ከመዝሙር 18 ጋር እንዴት ይዛመዳል?
2. መዝ. 144፡3 እና 4 ከመዝ. 144፡1 እና 2 ጋር እንዴት ይዛመዳሉ?
3. መዝ. 144፡5-7 “ከቅዱስ ጦርነት” ጋር እንዴት ይዛመዳል?
4. “ብዙ ውኆች” መዝ. 144፡7 ላይ ምንን ወይም ማንን ነው የሚጠቅሰው?
5. የኤምቲ መግቢያ ከመዝ. 144፡10 ጋር የማይጣጣመው ለምንድነው?
6. መዝ. 144፡12-14 ጸሎት ነው መግለጫ?

# መዝሙር 145
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር ስለ መልካምነቱ ሲከበር<br>ኤምቲ መግቢያ<br>የዳዊት መዝሙር | የእግዚአብሔር ግርማና ፍቅር መዝሙር | ውዳሴ የእስራኤልን አምላክ ባሕርይ የሚያሳይ<br>(መስቀልያ) | የምስጋና መዝሙር | ምስጋና ለያህዌ ለንጉሡ<br>(መስቀልያ) |
| 145:1-7 | 145:1-3 | 145:1-3 | 145:1-3 | 145:1-3 |
| | 145:4-7 | 145:4-7 | 145:4-9 | 145:4-5 |
| | | | | 145:6-7 |
| 145:8-13 | 145:8-9 | 145:8-9 | | 145:8-9 |
| | 145:10-13 | 145:10-13ለ | 145:10-13ለ | 145:10-11 |
| | | | | 145:12-13ለ |
| | | 145:13ሐ-20 | 145:13ሐ-16 | 145:13ሐ-14 |
| 145:14-16 | 145:14-16 | | | |
| | | | | 145:15-16 |
| 145:17-21 | 145:17-21 | | 145:17-20 | 145:17-18 |
| | | | | 145:19-20 |
| | | 145:21 | 145:21 | 145:21 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መስቀልያ መዝሙር ነው። ሌሎች ምሳሌዎችም መዝሙር ላይ አሉ።
1. መዝሙር 9 እና 10
2. መዝሙር 25
3. መዝሙር 34
4. መዝሙር 37
5. መዝሙር 111
6. መዝሙር 112
7. መዝሙር 119
8. መዝሙር 145

መስቀልያዎች ደግሞ ምሳ. 31፡16-31 እና ሰቆቃወ ኤርምያስ 1፤2፤3፤ እና 4 ላይ ሊታዩ ይችላሉ። 22 ፊደላት በዕብራይስጥ የፊደል ገበታ ላይ ይገኛሉ። በዚህ መዝሙር ላይ 21 ቁጥሮች ብቻ ነው የሚገኙት፣ ስለዚህ አንድ ፊደል መገደፉ ግልጽ ነው። የዕብራይስጡ "ኤን" ያለቦታው የተቀመጠ ይመስላል፣ በማሶረቲክ ጽሑፍ ላይ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽሑፋዊ ትንተና)። እሱም በሁሉም ጥንታዊ ቅጅዎች ላይ ተካትቷል — ሴፕቱዋጂንት፣ ቫልጌት፣ እና ፔሺታ። እሱን በአንደኛው የዕብራይስጥ ጽሑፍ ላይ እናገኘዋለን፣ በሙት ባሕር ጥቅሎች፣ 11ኪውፒኤስ[2]።

ለ. ይህ መዝሙር ስለ እስራኤል አምላክ ባሕርይና ያንን ባሕርይ ስለሚገልጠው ድርጊቱ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት።

ሐ. ይህ መዝሙር የተለየ ዩኒቨርሳላዊ ይዘት አለው፣ እሱም መዝ. 145፡8-21 ላይ ሊታይ የሚችል። ይህም የተለየ አጭር አመላካች ነው፣ የእግዚአብሔርን ልብ፣ በምድር ላይ ላሉት ሰዎች ሁሉ ያለውን ፍቅር የሚያሳይ፣ እናም ሰዎች ሁሉ በእምነት እንዲያውቁት ስለመሻቱ (ሕዝ. 18፡23፤32፤ዮሐንስ 3፡16፤4፡42፤1 ጢሞ. 2፡4፤4፡10፤ቲቶ 2፡11፤2 ጴጥ. 3፡9፤1 ዮሐንስ 2፡1፤4፡14፤ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡145፡1-7**

**[1]አምላኬ ንጉሤ ሆይ፥ ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ፥**
**ስምህንም ለዘላለም ዓለምም እባርካለሁ።**
**[2]በየቀኑ ሁሉ እባርክሃለሁ፥**
**ስምህንም ለዘላለም ዓለምም አመሰግናለሁ።**
**[3]እግዚአብሔር ታላቅ ነው እጅግም የተመሰገነ ነው**
**ለታላቅነቱም ፍጻሜ የለውም።**
**[4]ትውልደ ትውልድ ሥራህን ያመሰግናሉ፥**
**ኃይልህንም ያወራሉ።**
**[5]የቅድስናህን ግርማ ክብር ይናገራሉ፥**
**ተኣምራትህንም ይነጋገራሉ።**
**[6]የግርማህንም ኃይል ይናገራሉ፥ ታላቅነትህንም ይነጋገራሉ፥**
**ብርታትህንም ይነጋገራሉ።**
**[7]የቸርነትህን ብዛት መታሰብ ያወጣሉ፥**
**በጽድቅህም ሐሤትን ያደርጋሉ።**

**145፡1 "ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ"** ተደጋግሞ የተገለጸውን ግለሰባዊ ይዘት ተገንዘብ፣ መዝ. 145፡1-7 ላይ። ይህም በግልጽ ይታያል፣ "አምላኬ" በሚለው ሐረግ። ግልጽ የሆነው ነገር የግል እምነት የፍጥረትን አምላክ ለማወቅ የመጀመሪያው ነጥብ ነው፣ በታሪክም።

ይህ የመክፈቻ አንጓ (ማለትም፣ መዝ. 145፡1-7) በርካታ ተጓዳኞች አሉት።

1. ከፍ ከፍ አደርግሃለሁ፣ መዝ. 145፡1 – ቢዲቢ 926፣ ኬቢ 1202፣ *ፖለል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
2. ስምህንም አመሰግናለሁ፣ መዝ. 145፡1 – ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ *ፒል* ተጓዳኝ
3. እባርክሃለሁ፣ መዝ. 145፡2 – ቢዲቢ 138፣ ኬቢ 159፣ *ፒል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ
4. ስምህን አመሰግናለሁ፣ መዝ. 145፡3 – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ *ፒል* ተጓዳኝ
5. ተአምራትህንም እነጋገራለሁ፣ መዝ. 145፡5 – ቢዲቢ 967፣ ኬቢ 1319፣ *ቃል* ተጓዳኝ
6. ታላቅነትህንም እነጋገራለሁ፣ መዝ. 145፡6 – ቢዲቢ 707፣ ኬቢ 765፣ *ፒል* ያልተጠናቀቀ በተጓዳኝ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ

እውነተኛ ታማኝ ተከታዮች እምነታቸውንና ምስጋናቸውን ለያህዌ መግለጽ ይኖርባቸዋል።

▣ **"ንጉሤ ሆይ"** ያህዌ እውነተኛ የእስራኤል ንጉሥ ነው (1 ሳሙ. 8፡7)። ምድራዊው ንጉሥ የሰማያዊው ንጉሥ ተወካይ ብቻ ነው (መዝ. 10፡16፤ 29፡10፤98፡6)።

▣ **"ስምህን እባርካለሁ"** የ"መባረክ" ጽንሰ-ሐሳብ (ቢዲቢ 138–ግሥ፣ 139–ስም) የዕብራይስጥ ሥነ-መለኮት ክፋይ ነው፣ ከንግግር ቃል ኃይል ጋር በተያያዘ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ባርኮት (ብኪ)።

"ስም" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 1027) የዕብራውያን መንገድ ነው፣ ሰውን ለማመልከት። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ።

የእስራኤል አምላክ (መለኮት) *ኤሎሀ* ተብሎ ይጠራል፣ መዝ. 145፡1 ላይ፣ ነገር ግን ዘጠኝ ጊዜ በቀሪው መዝሙር ላይ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች።

▣ **"ለዘላለም ዓለምም"** ሐረጉ መዝ. 145፡1ለ እና 2ለ ላይ ጥቅም ላይ ውሏል፣ እናም በተመሳሳይ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ ይመስላል፣ መዝ. 34፡1 ላይ፣ ይኸውም መዝ. 145፡2ሀ ላይ ተለይቶ በግልጽ የተገለጸ። እሱ በርግጥ ከሞት በኋላ ላለው ሕይወት ማረጋገጫ አይደለም፣ ነገር ግን የዕብራይስጥ ፈሊጥ ነው፣ ለየቀኑ ምስጋና። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (ኦላም)።

**145፡3 "ለታላቅነቱም ፍጻሜ የለውም"** "ታላቅነት" የሚለው ስም (ቢዲቢ 153) ጥቅም ላይ የዋለው ለሁለቱም ነው

1. ለእግዚአብሔር ለራሱ – 1 ዜና. 29፡11፤መዝ. 48፡1፤86፡10፤147፡5
2. ለእርሱ ሥራ – 2 ሳሙ. 7፡21፤1 ዜና. 17፡19-21

"ፍጻሜ የሌለው" ("የማይመረመር" ማለትም፣ ስም አወቃቀር) ኢዮብ 5፡9፤9፡10፤11፡7። ተመሳሳይ ጽንሰ-ሐሳብ፣ የእግዚአብሔር መንገድ ከእኛ መረዳት በላይ መሆኑ መዝ. 40፡5፣28፤139፡6፤ኢሳ. 40፡28፤55፡8፣9፤ሮሜ. 11፡33 ላይ ተገልጿል።

**145፡4 "ትውልደ ትውልድ ሥራህን ያመሰግናሉ"** ይህም አጽንዖት የሚሰጠው እምነታቸውን ወደ ልጆቻቸው ማስተላለፋቸውን ነው (ዘዳ. 4፡9፣ 10፤6፡7፣20-25፤11፡19፤32፡7፣46፤መዝ. 22፡30፣31)።

የመዝ. 145፡4 ግሦች ያልተጠናቀቁ ናቸው፣ ነገር ግን በትርጉም ተጽዕኗዊ ይሆናሉ፣ የመዝሙረኛውን መሻት/ጸሎት በመግለጽ። በተመሳሳይ እውነትም መዝ. 145፡6 እና 7 (አኦት መጽሐፍ ቅዱስ፣ ገጽ 1009)።

▣ **"ብርቱ *ሥራህን*"** ይህ አጽንዖት ለእግዚአብሔር ነው፣ በታማኝነት ለኪዳን ተስፋው ለሚሠራው፣ መዝ. 145:4፤5፤6፤7፤12። ይህ ቃል ዘወትር የሚጠቀሰው የእግዚአብሔርን የቀድሞ የማዳን ሥራዎችን ነው፣ እንደ ዘጸአት ያሉትን።

**145፡5 "የቅድስናህን ግርማ ክብር"** የሰው ቃል ፈጽሞ በቂ አይደለም፣ የእግዚአብሔርን ክብር ለመግለጽ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ክብር [ብኪ])። እዚህጋ ተለጣጣቂ ቃላት አሉ፣ አንድ ላይ የተያያዙ፣ የእግዚአብሔርን ባለ-ግርማ ባሕርይ ለመግለጽ።

1. ድንቅ – ቢዲቢ 214፣ 1 ዜና. 16:27፤መዝ. 29:4፤90:16፤96:6፤104:1፤111:3፤ኢሳ. 2:10፤19፤21
2. ግርማ – ቢዲቢ 217፣ 1 ዜና. 16:27፤29:11፤መዝ. 96:6፤111:3፤148:13
3. ተአምራዊ – ቢዲቢ 810፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ተአምራት

▣ **"እነጋገራለሁ"** ታማኝ ተከታዮች የያህዌን ታላቅ ሥራዎች ያስባሉ፣ መዝ. 145፡7። አስገራሚ የሚሆነው መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ታማኝ ተከታዮች ምን ያህል ጊዜ እግዚአብሔር ያደረገውን እንዲያስታውሱ ማሳሰቢያ እንደሚሰጣቸው ነው!

**145፡6 "የግርማህንም ኃይል ይናገራሉ፥ ታላቅነትህንም ይነጋገራሉ፥"** ይህ የመጀመሪያው ጠቃሽ ነው፣ ለ"ሰዎች ሁሉ" ይኸውም የተለመደ አዝማች (ተደጋጋሚ) የመዝ. 145፡8-21። ይህም ዐውደ-ጽሑፋዊ አቅም አለው፣ አሕዛብን ሁሉ እንደሚያካትት፣ አይሁድንም ጭምር። ሆኖም፣ እሱ ጽሑፋዊ ፍላጎት ሊሆን ይችላል፣ በመስቀልያ የአጻጻፍ መልክ የተገኘ።

መዝሙረኛው የያህዌን ሥራዎች የሚጠቅስባቸውን መንገዶች ተገንዘብ።

1. ሥራዎችህ፣ መዝ. 145፡4ሀ፣ 9ለ፣ 10ሀ
2. ብርቱ ሥራዎችህ፣ መዝ. 145፡4ለ፣ 12
3. ተአምራትህን፣ መዝ. 145፡5ለ
4. የግርማህን ሥራዎች፣ መዝ. 145፡6ሀ

ይኸም የሚያመለክተው

1. ፍጥረት እና/ወይም የጥፋት ውኃ
2. የይቅርታ እና የመመለስ ድርጊት
3. የአብርሃምና የአባቶች መጠራት
4. ዘጸአት
5. ድል ማድረግ
6. በጦርነት ድል ማድረግ
7. ወዘተ.

**145፡7 "በብርቱ ይናገራሉ"** ግሡ (ቢዲቢ 615፣ ኬቢ 665፣ ሂፊል ያልተጠናቀቀ) ፍችው "ድምፅ ማሰማት" ማለት ነው። እሱም ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው በዘይቤአዊ መልኩ ነው (መዝሙር 19:2፤78:2፤119:171፣ 145:7)። እሱም ቋሚነት ያለው፣ በደስታ ስሜት ማወጅን የሚገልጽ ነው።

▣ **"ጽድቅህን"** "ጽድቅ" የሚለው ቃል (ቢዲቢ 842) የመጣው ከዕብራይስጥ ሥር ነው፣ "የመለኪያ ዘንግ።" እሱም በሁለት መንገዶች ጥቅም ላይ ይውላል፣ በብኪ፡

1. ለእግዚአብሔር ወሰን የሌለው ቅድስናና ዘላለማዊነት
2. ለእርሱ እስራኤልን የመዋጀት ሥራ

ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ።

***መዝሙር*** **፡145፡8-13**

**[8]እግዚአብሔር ርኅሩኅና መሓሪ ነው፥**
**ከቍጣ የራቀ፥ ምሕረቱም ብዙ ነው**
**[9]እግዚአብሔር ለሚታገሡት ቸር ነው።**
**ምሕረቱም በሥራው ሁሉ ላይ ነው።**
**[10]አቤቱ፥ ሥራህ ሁሉ ያመሰግኑሃል፥**
**ቅዱሳንህም ይባርኩሃል።**
**[11]የመንግሥትህን ክብር ይናገራሉ፥**
**ኃይልህንም ይነጋገራሉ፥**
**[12]ለሰው ልጆች ኃይልህን**
**የመንግሥትህንም ግርማ ክብር ያስታውቁ ዘንድ**
**[13]መንግሥትህ የዘላለም መንግሥት ናት፥**
**ግዛትህም ለልጅ ልጅ ነው።**

**145፡8 "እግዚአብሔር ርኅሩኅና መሓሪ ነው፥**

**ከቊጣ የራቀ፥ ምሕረቱም ብዙ ነው"** ይህ ቀጥተኛ ጥቅስ ነው ከዘጸአት 34፡6፣7 እና መዝ. 103፡8 ላይ ተደግሟል። እሱም የእግዚአብሔርን ባሕርይ ብቻ አይገልጽልንም፣ ነገር ግን እንደገና በታሪክ ላይ አንዱን ብርቱ ሥራውን ያሳየናል እንጂ፣ ከርኅራኄው የሚነሣውን፣ በሰው ሥራ ሳይሆን (ማለትም፣ ዘጸአት)። ልቱ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት።

**145፡9 "እግዚአብሔር ለሚታገሡት ቸር ነው።**
**ምሕረቱም በሥራው ሁሉ ላይ ነው።"** እግዚአብሔር ለሰዎች ዘላለማዊ ፍቅር አለው በአምሳሉ ለተፈጠሩት (ዘፍ. 1:26፣27፤3:8)። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ።

**145፡10 "አቤቱ፥ *ሥራህ ሁሉ ያመሰግኑሃል፥*"** ይሄንን ከመዝ. 103፡19-22 ጋር አነጻጽር።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ** | ***"ቅዱሳን"*** |
| **አኪጀቅ፣ ፔሺታ** | ***"ጻድቃን"*** |
| **አየተመቅ፣ አኢመቅ** | ***"ታማኝ"*** |
| **አእቅ** | ***"ሰዎች"*** |
| **ጀፒኤስኦኤ** | ***"የታመኑት"*** |
| **የተእመቅ** | ***"ታማኝ ባሪያዎች"*** |
| **LXX** | ***"የተሰጡ"*** |

ይህ የዕብራይስጥ ቅጽል (ቢዲቢ 339) የተመሠረተው በ ﬢסח ሥር ላይ ነው፣ ("*ሄሰድ?*" ቢዲቢ 338፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት [ሄስድ])። እሱም ባመዛኙ ጥቅም ላይ የሚውለው ለታማኝ የኪዳን ተከታዮች ነው (1 ሳሙ. 2:9፤መዝ. 4:3፤12:1፤30:4፤31:24፤37:28፤50:5፤79:2፤85:8፤86:2፤89:19፤97:10፤116:15፤145:10፤148:14፤149:9)፣ ግን ደግሞ ሊጠቅስ ይችላል

1. ካህናትን – ዘዳ. 33:8፤2 ዜና. 6:4፤መዝ. 132:16
2. መሲሑን – መዝ. 16:10
3. የሰማያዊውን ጉባኤ መላእክትን – መዝ. 29:1፤103:19-22፤148:2፤እና ይህ አንጓ

**145:11-12** እነዚህ ቁጥሮች የሚያመለክቱት

1. መልአካዊ ውዳሴ – ቁ. 3ን ተመልከት መዝ. 145:10 ላይ
2. የታማኝ ተከታዮች ተግባር፣ ያህዌ በዘዎች ሁሉ ዘንድ እንዲታወቅ (ማለትም፣ "የሰው ልጆች")

የትኛው እንደሚመረጥ ለመወሰን አዳጋች ነው። ቁጥር 1 የሚወክለው ፍጥረት ሁሉ ፈጣሪውን ሲያከብር ነው (መዝ. 103፡19-22) እና ቁጥር 3 የአብርሃምን መጠራት ዓላማ ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የመዋጀት ዕቅድ)።

**145፡13 "*መንግሥትህ የዘላለም መንግሥት ናት፥*"** ይህ የዘላለም መንግሥት ጽንሰ-ሐሳብ መዝ. 10:16፤29:10፤ኢሳ. 9:6-7፤ዳን. 2:44፤4:3፣34፤6:26፤7:14፣26፤2 ጴጥ. 1:11 ላይ ይገኛል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእግዚአብሔር መንግሥት።

▣ ***"ሥራ"*** ይህ ነው አብዛኞቹ ዘመናዊ ትርጉሞች የጠፋውን ነን (*nun*) ሐረግ የከተቱበት፣ ከLXX፣ ፔሺታ እና ቫልጌት፣ እና የሙት ባሕር ጥቅሎች የዕብራይስጥ ጽሑፎች ላይ (ማለትም፣ 11ኪውፒኤስ[a])፣ "እግዚአብሔር በቃሉ ሁሉ ታማኝ ነው፣ በሥራው ሁሉ ባለጸጋ ነው።" ይህም ከመዝ. 145፡17 ጋር እጅግ ተመሳሳይ ነው።

## *መዝሙር* ፡145፡14-16

> **14 እግዚአብሔር በቃሎቹ የታመነ ነው፥**
> **በሥራውም ሁሉ ጻድቅ ነው**
> **እግዚአብሔር የተፍገመገሙትን ሁሉ ይደግፋቸዋል፥**
> **የወደቁትንም ያነሣቸዋል።**
> **15 የሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል**
> **አንተም ምግባቸውን በየጊዜው ትሰጣቸዋለህ።**
> **16 አንተ እጅህን ትከፍታለህ፥**
> **ሕይወት ላለውም ሁሉ መልካምን ታጠግባለህ።**

**145:14 "*የእግዚአብሔር ወደቁትን ያነሣቸዋል።*"** መዝሙር 145:14-16 የሚናገረው እግዚአብሔር የታማኝ ተከታዮችን ሥጋዊ ፍላጎቶች የሚያሟላ ሲሆን፣ መዝ. 145:17-21 ደግሞ የሚናገረው እግዚአብሔር ለመንፈሳዊ ፍላጎታቸው የሚሰጥ መሆኑን ነው። "ሁሉም" የሚለውን ቃል ተደጋጋሚ አጠቃቀም ተገንዘብ።

**145:15 "*የሁሉ ዓይን አንተን ተስፋ ያደርጋል*"** እነዚህ ቁጥሮች የሚያስቀምጡት እግዚአብሔር ለፍጥረቱ ሁሉ ምግብ እንደሚሰጥ ነው፣ መዝ. 104:27፣28፤136:25።

**145:16** ይህ "የመጋቢነት" ጽንሰ-ሐሳብ ነው። እግዚአብሔር ይህንን ዓለምና ሁሉንም የእርሱን ሕይወት መልክ ፈጥሯል፣ ይመግባልም። ይህ ድርጊት በብኪ አስተዋጽዖው የተሰጠው ለኤሎሂም ነው (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የመለኮት ስሞች)።

**መዝሙር ፡145፡17-21**

[17]**እግዚአብሔር በመንገዱ ሁሉ ጻድቅ ነው**
**በሥራውም ሁሉ ቸር ነው።**
[18]**እግዚአብሔር ለሚጠሩት ሁሉ፥**
**በእውነት ለሚጠሩት ሁሉ ቅርብ ነው።**
[19]**ለሚፈሩት ምኞታቸውን ያደርጋል፥**
**ልመናቸውንም ይሰማል ያድናቸዋልም።**
[20]**እግዚአብሔር የሚወድዱትን ሁሉ ይጠብቃል**
**ኃጢአተኞችንም ሁሉ ያጠፋል።**
[21]**አፌ የእግዚአብሔርን ምስጋና ይናገራል**
***ሥጋም ሁሉ ለዘላለም ዓለም የተቀደሰውን ስሙን ይባርክ።***

**145፡17 "በሥራውም ሁሉ ቸር ነው።"** ይህ የዕብራይስጥ ቃል *ሄሰድ* ነው፣ ስለ እግዚአብሔር የኪዳን ታማኝነት የሚናገር። እሱም ቀደም ብሎ በመዝ. 145፡8 ጥቅም ላይ ውሏል፣ የእግዚአብሔርን ባሕርይ ለመግለጽ፣ እዚህ ደግሞ የእግዚአብሔርን ድርጊቶች ለመግለጽ።

**145፡18 "ጌታ ቅርብ ነው"** ይህ አጽንዖት የሚሰጠው ለእግዚአብሔር ታላቅነት ሲሆን፣ መዝ. 145፡5 ደግሞ የእርሱን ወሰን-የለሽነት ይገልጻል፣ መዝ. 34:18፤119:151፤እና በተለይ ዘዳ. 4:7።

▣ **"ለሚጠሩት ሁሉ"** ተለጣጣቂ ሁኔታዎች አሉ (ማለትም፣ መዝ. 145፡18-20)። መታወስ የሚኖርበት ሁሉም የእግዚአብሔር ኪዳናት በእርሱ በኩል ሁኔታዊ አለመሆናቸው ነው፣ ነገር ግን በሰው ምላሽ በኩል ሁኔታዊ ናቸው። እነዚህ አራት ሁኔታዎች የሚናገሩት ስለ ንስሐ እና እምነት ነው፣ በሁለቱም በመነሻም ሆነ በቀጣይነት፣ በእግዚአብሔር ሕዝብ በኩል። ማስታወሻ ተመልከት፣ ሮሜ. 10፡9-13 ድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ላይ።

**145፡19 "የሚፈሩት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፍርሃት (ብኪ)።

**145፡20 "ኃጢአተኞችንም ሁሉ ያጠፋል።"** ይህ በሞት ስለ ማጥፋት የሚናገር አይደለም ነገር ግን ሥጋዊ ፍርድን እንጂ፣ ሕዝ. 14:9፤አሞጽ 9:8፤ ዕን. 2:2 (የሮበርት ጊርድልስቶንን፣ *የብሉይ ኪዳን ተመሳስሎን* ተመልከት፣ ገጽ 178 ላይ)።

**145፡21 "*ሥጋም ሁሉ ለዘላለም ዓለም የተቀደሰውን ስሙን ይባርክ።*"** ይህ በድጋሚ እንደ መዝ. 145፡1 እና 3 ዓይነት ነው። እሱም ከሞት በኋላ ላለ ሕይወት ማረጋገጫ አይደለም፣ ነገር ግን የርግጠኝነቱ አንድምታ ተቀምጧል፣ ፊሊ. 2፡6-11 ላይ እንዳለው።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. ለእግዚአብሔር አስተዋጽዖ የሚገባውን ምስጋና ዘርዝር።
2. ይህ መዝሙር የእግዚአብሔርን ድርጊቶች በብዙ ቁጥሮችና በብዙ መንገዶች ይገልጻል። ምን ዓይነት ድርጊቶችን ነው የሚጠቅሰው?
3. መዝ. 145፡8-16 (እና 145፡21) የእግዚአብሔርን ዩኒቨርሳላዊ ፍቅር እንዴት ያመለክታሉ?
4. "ጻድቃን" እነማናቸው፣ መዝ. 145፡10 ላይ?
5. "የሰው ልጆች" እነማናቸው፣ መዝ. 145፡12 ላይ?
6. ብኪ የሚያተኩረው ዘላለማዊ መንግሥት ላይ ነው ወይስ ሚሊኒየማዊ?
7. የመዝ. 145፡5 "ወሰን የለሽነት" ከመዝ. 145፡18 "ታላቅነት" ጋር እንዴት ይዛመዳል?
8. አራቱን የመዝ. 145፡18-20 ሁኔታዎች ዘርዝር ከታማኝ ተከታዮች ጋር የሚያያዙትን።

# መዝሙር 146
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እግዚአብሔር ቸሩ ረዳት<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | ርዳታቸው በጌታ የሆነ የእነርሱ ደስታ | ውዳሴ እግዚአብሔርን በማመስገን ስለ ዕርዳታው | እግዚአብሔርን ማመስገን አዳኙን | እግዚአብሔርን ስለ ዕርዳታው ማወደስ |
| 146:1-7 | 146:1ሀ | 146:1-2 | 146:1-2 | 146:1-2 |
| | 146:1ለ-2 | | | |
| | 146:3-4 | 146:3-4 | 146:3-4 | 146:3-4 |
| | 146:5-7 | 146:5-7ለ | 146:5-7ለ | 146:5-6ለ |
| | | | | 146:6c-7 |
| | | 146:7ሐ-9 | 146:7ሐ-9 | |
| 146:8-10 | 146:8-9 | | | 146:8-9 |
| | | | | 146:8ሐ |
| | | | | 146:9ሐ |
| | 146:10 | 146:10 | 146:10 | 146:10 |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡146፡1-7**

**1ሃሌ ሉያ።**
**ነፍሴ ሆይ፥ እግዚአብሔርን አመስግኚ።**
**2በሕይወቴ እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ**
**በምኖርበት ዘመን ሁሉ ለአምላኬ እዘምራለሁ።**
**3ማዳን በማይችሉ በሰው ልጆችና**
**በአለቆች አትታመኑ።**
**4ነፍሱ ትወጣለች ወደ መሬቱም ይመለሳል**
**ያን ጊዜ ምክሩ ሁሉ ይጠፋል።**
**5የያዕቆብ አምላክ ረዳቱ የሆነ**
**ተስፋውም በአምላኩ በእግዚአብሔር የሆነ ሰው ምስጉን ነው**
**6እርሱም ሰማይንና ምድርን**
**ባሕርንም፥ በእነርሱ ያለውንም ሁሉ የፈጠረ**
**እውነትን ለዘላለም የሚጠብቅ**
**7ለተበደሉት የሚፈርድ፥**
**ለተራቡ ምግብን የሚሰጥ ነው።**
**እግዚአብሔር የታሰሩትን ይፈታል**

**146፡1-2** ይህ አንጓ (መዝ. 146፡1-7) የሚጀምረው በድርብ ሃሌ ሉያ ነው (ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ፒል ተተኳሪS)። ይንንም ሁለት ግለሰባዊ ግዳጆች ይከተሉታል፣ የመዝሙረኛው።

1. አመሰግናለሁ – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ፒል ተጓዳኝ
2. ምስጋና እዘምራለሁ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ፒል ተጓዳኝ)

የያህዌ ባሕርያት ምስጋና፣ መዝሙር 146-150። መዝሙሩ የሚያበቃው በዚህ አጽንዖት ነው።

**146፡1 "ነፍስ"** ይህ ቃል ኔፈሽ ነው (ቢዲቢ 659)፣ እሱም የሰውን ሙሉ ቁመና የሚገልጽ (መዝ. 103፡1)። ማስታወሻ ተመልከት በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር ዘፍ. 35፡18 ላይ።

**146፡2** በመካካል ያሉትን ትይዩዎች ተመልከት

1. በሕይወቴ – ቢዲቢ 313
2. በምኖርበት ዘመን ሁሉ – ቢዲቢ 728

እነዚህ የዕብራይስጥን ጽንሰ-ሐሳብ ያንጸባርቃሉ፣ ከሞት በኋላ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደማይኖር (ኢዮብ 10:21-22፤38:17፤መዝ. 63:4፤ 104:33፤ኢሳ. 38:18)። ብኪ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት በውል ያልተደራጀ ሥነ-መለኮት ነው ያለው። የአዲስ ኪዳን ቀጣይነት ያለው መገለጥ ይሄንን ሥነ-መለኮት ያጠናከረዋል። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሲኦል።

**146፡3** እግዚአብሔር ሊመሰገን ይገባል፣ ምክንያቱም በእርሱ፣ እና እሱ ብቻ ደኅንነት/መዳን ስለሆነ (ቢዲቢ 448)፣ በርግጥም በደካማ፣ በወደቀ የሰው ልጅ አይደለም (ኤምቲ፣ "የሰው ልጅ"፤ LXX፣ "የሰው ልጆች"፤ መዝሙር 60፡11፤ 108፡12)። ነጠላው የሚሆነው ለሰዎች ሁሉ ነው፣ እንደ መዝ. 118፡8፡።

**146፡4** ይህ ቁጥር የመዝ. 146፡2ን ሐሳብ ያነሣል። በሞት ሥጋ ወደ አፈሩ ይመለሳል (ዘፍ. 3:19፤ኢዮብ 34:15፤መዝ. 104:29፤መክ. 12:7)። ነፍስ (ሩሕ፣ ቢዲቢ 924) የሕይወት ኃይል ወደ ሲኦል ይሄዳል።

▣ **"ሐሳቡ"** ይህ ቃል (ቢዲቢ 799) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ ብኪ ላይ፣ እናም ባብዛኞቹ ዘመናዊ ትርጉሞች የሚተረጎመው "ዕቅድ/ንድፍ" በሚል ነው።

**146፡5** መዝሙሩ እግዚአብሔርን ያመሰግናል፣ ግን ደግሞ እንዴት እንደ "ተባረኩ" ያሳያል (ቢዲቢ 80) ታማኝ ተከታዮች። መዝሙር 146፡6-7 እና 8-9 የያዕቆብን አምላክ ኃይልና ምሕረት ይዘረዝራል።

▣ **"ዕርዳታ"** ይህ ስም (ቢዲቢ 740 I) ዘወትር የሚያያዘው ከመታደግና ከጥበቃ ጋር ነው (ዘጸ. 18:4፤ዘዳ. 33:7፣26፤መዝ. 33:20፤70:5፤115:9፣10፣11)።

▣ **"ተስፋ"** ስሙ (ቢዲቢ 960 II) ሊተረጎም ይችላል

1. መጠበቅ – መዝ. 104:27፤145:15
2. ተስፋ ማድረግ – መዝ. 119:166፣ ኢሳ. 38:18

**146:6-7** ተለጣጣቂ የሆኑ ቃል አንቀጾች (ግሥ) አሉ ያህዌን የሚገልጹ

1. እንደ ፈጣሪ (ማለትም፣ ኤሎሂም)
   ሀ. ሰማይ፣ ምድርን፣ ባሕርን የሠራ፣ መዝ. 115:15፤121:2፤124:8፤134:3፤ኢሳ. 37:16፤ኤር. 32:17
   ለ. በእነርሱ ውስጥ ያለውን ሁሉ የፈጠረ
   ሐ. ይህ የማጠቃለያ መግለጫ ነው፣ ከዚህ ፕላኔት ጋር የሚያያዝ
2. እንደ ኪዳን አምላክ (ማለትም፣ ያህዌ)
   ሀ. እምነትን/መታመንን ይጠብቃል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ማመን፣ መታመን፣ እምነት እና ታማኝነት በብኪ)
   ለ. ለተበደሉት የሚፈርድ (አእመቅ እና የተእመቅ "ዘላለም" ተመልከት፣ לְעוֹלָם ፣ የመዝ. 146:6ሐ እንደ "የተበደሉ፣" לְעוֹלָם ፣ ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት፣ ገጽ 440)
   ሐ. ለተራቡት ምግብን የሚሰጥ፣ መዝ. 145:15
   መ. የታሰሩትን ይፈታል፣ መዝ. 68:6፤102:20፤107:10፣14፤ኢሳ. 61:1
      (1) የችግሮች ዘይቤ
      (2) በዕዳ ምክንያት ባርነት
      (3) ግዞት

**መዝሙር ፡146፡8-10**

**[8]እግዚአብሔር የወደቁትን ያነሣል**
**እግዚአብሔር ዕውሮችን ጥበበኞች ያደርጋቸዋል**
**እግዚአብሔር ጻድቃንን ይወድዳል**
**[9]እግዚአብሔር ስደተኞችን ይጠብቃል**
**ድሀ አደጎችንና ባልቴቶችን ይቀበላል**
**የኃጢአተኞችንም መንገድ ያጠፋል።**

[10]**እግዚአብሔር ለዘላለም ይነግሣል**
**ጽዮን ሆይ፥ አምላክሽ ለልጅ ልጅ ነው።**
**ሃሌ ሉያ።**

**146፡8-9** እንደ መዝ. 146፡6-7፣ እነዚህም ቁጥሮች የሚሠራውን አምላክ ይገልጻሉ፣ ሕይወት-አልባ ከሆኑት ጣዖታት እጅግ የሚለይ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የእስራኤል አምላክ ባሕርያት)።

1. ዕውር ዓይኖችን ይከፍታል– ቢዲቢ 824፣ ኬቢ 959፣ *ቃል አንቀጽ*
2. የወደቁትን ያነሣል – ቢዲቢ 279፣ ኬቢ 279፣ *ቃል አንቀጽ*፣ መዝ. 145:14 (እነዚህ ብቸኞቹ የግሡ አጠቃቀሞች ናቸው፣ ብኪ ላይ)
3. ጻድቃንን ይወድዳል – ቢዲቢ 12፣ ኬቢ 17፣ *ቃል አንቀጽ*፣ መዝ. 11:7፤33:5
4. ስድተኞችን ይጠብቃል – ቢዲቢ 1036፣ ኬቢ 1581፣ *ቃል አንቀጽ* (ለተሻለ አጭር አንቀጽ የ ሮላድ ዲ ቫኡክስን የጥንቱ እስራኤል፣ ገጽ 74-76 ተመልከት)
5. ደሀ-አደጎችንና ባልቴቶችን ይደግፋል – ቢዲቢ 728፣ ኬቢ 795፣ *ፒል ያልተጠናቀቀ*
6. የኃጢአተኞችን መንገድ ያጠፋል – ቢዲቢ 736፣ ኬቢ 804፣ *ፒል ያልተጠናቀቀ*

ይህ ዝርዝር የእግዚአብሔር ሥራ ቅንብር ነው፣ ከሌዋውያን፣ ከዘዳግም፣ እና ከነቢያት።

ቁጥር 6 በጥሬው "ማጎንበስ" ነው (ቢዲቢ 736) ወይም "መጣመም።" ይህም የቃላት መዘዋወር ሊሆን ይችላል፣ "ጻድቅ" የመዝ. 146፡8ሐ፣ እሱም ፍችው "ቀና መሆን" የሚል (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽድቅ)። ሁሉም ለኃጢአት የሆኑት ቃላት የዚህ ዘይቤ መዘዋወር ናቸው፣ ለእግዚአብሔር ባሕርይ፣ የሰው ልጆች ሁሉ ጠማማ ከመሆናቸው አኳያ።

**146፡10** ይህ የሚናገረው ስለ እስራኤል አምላክ ሉዓላዊነትና ስለ ዕቅዱ ነው (ዘጸ. 15:18፤መዝ. 10:16፤29:10)።

ለሥነ-መለኮታዊ ማስታወሻ ያህል፣ ያህዌ እንዴት ይነግሣል፣ የትና በማን ላይ? አባክዎትን ልዩ ርዕስ ይመልከቱ፡ የብኪ ኪዳን ተስፋዎች ከአኪ ኪዳን ተስፋዎች እጅግ የተለዩ የሚመስሉት ለምንድነው?

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጉመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. እስራኤላውያን ከሞት በኋላ ምን ይጠብቁ ነበር (መዝ. 146፡2፤4)?
2. መዝ. 146፡6 የሚናገረው ስለ ዩኒቨርስ ነው ወይስ ስለዚህ ዓለም?
3. የእግዚአብሔር ባሕርይና ድርጊት ስዕላዊ ገለጻ ከጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ)፣ ንጉሥ እንዴት ማድረግ እንደሚኖርበት ከሚገልጸው አስተሳሰብ ጋር እንዴት ይዛመዳል?
4. ያህዌ በጽዮን/ከጽዮን ይነግሣልን ወይስ ግዛቱ ዩኒቨርሳላዊ ነው? አኪ ይሄንን የብኪ ጽንሰ-ሐሳብ እንዴት ቀየረው?

# መዝሙር 147
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ምስጋና ለኢየሩሳሌም መመለስና ብልጽግና<br><br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | ምስጋና ለእግዚአብሔር ስለ ቃሉና ጠባቂነቱ | የምስጋና ውዳሴ ለጌታ ስለ ዩኒቨርሳላዊ ኃይሉና ጥበቃዊ ክብካቤው | ምስጋና ለሉዓላዊው አምላክ | ውዳሴ በሁሉም ብርቱ ለሆነው |
| 147:1-6 | 147:1 | 147:1-6 | 147:1-3 | 147:1-4 |
| | 147:2-6 | | 147:4-6 | |
| | | | | 147:5-6 |
| 147:7-11 | 147:7-9 | 147:7-11 | 147:7-9 | 147:7-9 |
| | 147:10-11 | | 147:10-11 | 147:10-11 |
| 147:12-20 | 147:12-14 | 147:12-20 | 147:12-14 | 147:12 |
| | | | | 147:13-14 |
| | 147:15-18 | | 147:15-18 | 147:15-16 |
| | | | | 147:17-18 |
| | 147:19-20ሐ | | 147:19-20ለ | 147:19-20ለ |
| | 147:20መ | | 147:20ሐ | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፤147፤1-6**

**[1]እግዚአብሔርን አመስግኑ፥**
**መዝሙር መልካም ነውና።**
**ለአምላካችን ምስጋና ያማረ ነው።**
**[2]እግዚአብሔር ኢየሩሳሌምን ይሠራል፥**
**ከእስራኤልም የተበተኑትን ይሰበስባል።**
**[3]ልባቸውን የቈሰሉትን ይፈውሳል፥**
**ሕማማቸውንም ይጠግናል።**
**[4]የከዋክብትንም ብዛት ይቈጥራል፥**
**ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል።**
**[5]ጌታችን ታላቅ ነው፥ ኃይሉም ታላቅ ነው፥**
**ለጥበቡም ቍጥር የለውም።**
**[6]እግዚአብሔር የዋሃንን ያነሣል፥**
**ኃጢአተኞችን ግን እስከ ምድር ድረስ ያዋርዳል።**

**147:1-6** ይህ የመጀመሪያ አንጓ (መዝ. 147:1-6)፣ እንደ መዝሙር 146፣ በርካታ የእግዚአብሔርን ባሕርያት ይዘረዝራል፣ ይኸውም በሥራው የሚረጋገጥ (ይህ መዝሙር ድኅረ-ስደት ነው)።
1. ለእስራኤል
   ሀ. ኢየሩሳሌምን ይሠራል
   ለ. ከእርሷ የተበተኑትን ይሰበስባል (ማለትም፣ ስደተኞች፣ ኢሳ. 11:12፤ ሕዝ. 39:28)
2. ለችግረኞች
   ሀ. ልባቸውን የቆሰሉትን ይፈውሳል (በስደት ጊዜ ንስሐ የገቡትን እስራኤላውያንን ሊሆን ይችላል፣ መዝ. 51:17፤18)
   ለ. የተቸገሩትን ይረዳል (ማለትም፣ ዘወትር ለታማኝ ተከታዮች ጥቅም ላይ የሚውል)
   ሐ. ኃጢአተኞችን ያዋርዳል
      (1) የባዕዳን ሕዝቦች
      (2) ያልታመኑ የኪዳን ተካፋዮች
3. አምልኮ ጣዖትነትን በመቃወም (ማለትም፣ የአስትራል ጣዖት አምልኮ)
   ሀ. የከዋክብትን ብዛት ይቆጥራል (ዘፍ. 1:16፤ ኢሳ. 40:26፣ ማለትም፣ አማልክትን ሳይሆን፣ መዝ. 8:3
   ለ. እነርሱን በስማቸው ይጠራል (ማለትም፣ ይቆጣጠራቸዋል)
   ሐ. እግዚአብሔር ኃይሉ ታላቅ ነው (ኢሳ. 40:26ሠ)
   መ. እግዚአብሔር ለማስተዋሉ ወሰን የለውም (ቢዲቢ 108፣ ኢሳ. 40:28)

**147:1**
**አአመመቅ** **"መልካም"**
**አኪጀቅ** **"ውብ"**
**አእቅ፣ የተእመቅ** **"የተገባ"**
**ጀፒኤስአኤ** **"ባለ ግርማ"**

ይህ ቅጽል (ቢዲቢ 610) ፍችው የሚሆነው
1. ውብ – ሰሎ. 1:5፤2:14፤4:3፤6:4
2. የተገባ፣ ተገቢ የሆነ እግዚአብሔርን ለማመስገን – መዝ. 33:1፤93:5፤ምሳ. 17:7

**147:4ለ "ሁሉንም በየስማቸው ይጠራቸዋል።"** አንድን ነገር መሰየም በእርሱ ላይ ያለ ሥልጣንን ያመላክታል (ዘፍ. 2:18-20)።

**147:6 እስከ ምድር ድረስ"** ይህን በበርካታ መንገዶች መረዳት ይቻላል።
1. የተሸነፈ ጠላት እስከ ምድር ድረስ አጎንብሶ
2. በተዘዋዋሪ መንገድ ሞትን/ሲኦልን መጥቀሻ

**መዝሙር :147:7-11**

**[7]ለእግዚአብሔር በምስጋና ዘምሩ፥**
**ለአምላካችንም በመሰንቆ ዘምሩ**
**[8]ሰማዩን በደመናት ይሸፍናል**
**ለምድርም ዝናብን ያዘጋጃል**
**ሣርን በተራሮች ላይ ያበቅላል ለምለሙንም ለሰው ልጆች ጥቅም።**
**[9]ለሚጠሩት ለቍራዎች ጫጩቶች**
**ለእንስሶችም ምግባቸውን ይሰጣል።**
**[10]የፈረስን ኃይል አይወድድም፥**
**በሰውም ጭን አይደሰትም።**
**[11]እግዚአብሔር በሚፈሩት፥**
**በምሕረቱም በሚታመኑት ይደሰታል።**

**147:7-11** የመጀመሪያው አንጓ በ "ምስጋና" እንደሚጀምር ሁሉ (ፒል ተተኳሪ)፣ ይኼኛውም (መዝ. 147:7-11) በ "ዝማሬ" ይጀምራል።
1. ዘምሩ – ቢዲቢ 777፣ ኬቢ 854፣ ቃል ተተኳሪ
2. ምስጋና ዘምሩ – ቢዲቢ 274፣ ኬቢ 273፣ ፒል ተተኳሪ

የዚህ ዝማሬ ርዕሰ-ጉዳይ ያህዌ እና የእርሱ ታላቅ ሥራ ነው።
1. እንደ ፍጥረት መጋቢ እና የተለመደውን የተፈጥሮ ዑደት ሰጭ (መዝ. 104:10-17)
   ሀ. ደመናት
   ለ. ዝናብ
   ሐ. የዕጽዋት እድገት
   መ. ምግብ ለእንስሳት (መዝ. 104:27ለ፤136:25)
2. የማይታመናቸው እና የሚታመናቸው
   ሀ. አሉታዊ (መዝ. 33:16-17)
      (1) ወታደራዊ ኃይል (ማለትም፣ ፈረስ)
      (2) የሰው ብርታት (ማለትም፣ ጭን/ቅልጥም)
   ለ. አዎንታዊ

(1) በሚፈሩት (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ፍርሃት [ብኪ]) እሱን
(2) የእርሱን ምሕረት በሚጠባበቁ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት [ሄስድ])

**147፡9ለ** ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት (ገጽ 1176) ባህላዊ ምሳሌ ይጠቅሳል፣ ቁራዎች ጫጩቶቻቸውን በአግባቡ እንደማይመግቡ (ኢዮብ 38፡41)፣ ነገር ግን እዚህ የሚያስረግጠው ርኅሩኅ መጋቢ እግዚአብሔር እንደሚያደርግ ነው!

ደግሞም ጠቃሚ ሊሆን የሚችለው፣ ቁራ (ቢዲቢ 788) የሚቆጠረው ንጹሕ እንዳልሆነ ወፍ ነው (ሌዋ. 11፡15) እግዚአብሔር ግን ለእነርሱም ይጠነቀቃል!

---

***መዝሙር ፡147፡12-20***

**[12]ኢየሩሳሌም ሆይ፥ እግዚአብሔርን አመስግኚ፥**
**[13]ጽዮንም ሆይ፥ ለአምላክሽ እልል በዪ**
**የደጆችሽን መወርወሪያ አጽንቶአልና፥**
**ልጆችንም በውስጥሽ ባርኮአልና።**
**[14]በወሰንሽም ሰላምን አደረገ፥**
**የስንዴንም ስብ አጠገበሽ።**
**[15]ነገሩን ወደ ምድር ይሰድዳል፥**
**ቃሉም እጅግ ፈጥኖ ይሮጣል።**
**[16]አመዳዩን እንደ ባዘቶ ይሰጣል**
**ጉሙን እንደ አመድ ይበትነዋል**
**[17]በረዶውን እንደ ፍርፋሪ ያወርዳል**
**በበረዶውስ ፊት ማን ይቆማል?**
**[18]ቃሉን ልኮ ያቀልጠዋል**
**ነፋሱን ያነፍሳል፥ ውኆችንም ያፈስሳል።**
**[19]ቃሉን ለያዕቆብ፥**
**ሥርዓቱንና ፍርዱን ለእስራኤል ይናገራል።**
**[20]ለሌሎች አሕዛብ ሁሉ እንዲህ አላደረገም፥**
**ፍርዱንም አልገለጠላቸውም።**
**ሃሌ ሉያ።**

---

**147፡12-20** ይህ ሦስተኛ አንጓ (መዝ. 147፡12-20) ደግሞ የሚጀምረው በምስጋና ተተኳሪዎች ነው።
1. አመስግኚ – ቢዲቢ 986፣ ኬቢ 1387፣ ፒል ተተኳሪ
2. አመስግኚ – ቢዲቢ 237፣ ኬቢ 248፣ ፒል ተተኳሪ

ምስጋና ለእርሱ ይገባል፣ ስለ ኪዳን ታማኝነቱ (በተለይ፣ ሌዋውያን 26፤ ዘዳግም 27-30) ለእስራኤል (ማለትም፣ ኢየሩሳሌም... ጽዮን)።
1. የኢየሩሳሌምን ደጆች መወርወሪያ አጽንቷልና (ማለትም፣ ደጅ መወርወሪያ)
2. ባርኳልና
   ሀ. የከተማይቱን ልጆች (ማለትም፣ ጤና፣ ቁጥራቸውን)
   ለ. በከተማይቱ ውስጥ ያሉትን ሰዎች (አእት)
3. ለምድሪቱ ሰላምን ያመጣል
4. መልካም አዝመራ ይሰጣል
5. የአየር ሁኔታውን ይቆጣጠራል (መዝ. 147፡16-18) የተትረፈረፈ የግብርና ምርት እንዲያገኙ (ማለትም የኪዳን ተስፋዎች፣ መዝ. 147፡19)
6. የእርሱ ልዩ ግንኙነት (ማለትም፣ ራዕይ) ለአብርሃም፣ ይስሐቅ፣ ያዕቆብ ዘሮች ጋር

**147፡14ለ "የስንዴ ስብ"** ይህ የግብርና በረከት ዘይቤ ነው (መዝ. 81፡16) ምክንያቱም እህል ዋነኛው የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ምግብ ከመሆኑ የተነሣ።

**147፡15** የእግዚአብሔር ቃል በፍጥነት እንደሚሮጥ ያለ ሰውኛ ሆኗል (ማለትም፣ ወደ ፍጥረት ሁሉ እንደሚሄድ)። በዕብራይስጥ አስተሳሰብ የእግዚአብሔር ቃል የፈጠራ ኃይል ነበር (ዘፍጥረት 1)። አንዴ ከተሰጠ ዓላማውን ይፈጽማል (ኢሳ. 45:23፤55:11)።

**147:19 "ቃል. . .ሥርዓት. . .ፍርድ"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቃላት ለእግዚአብሔር ራዕይ።

**147:19 "አላወቋቸውም"** የእግዚአብሔር ራዕይ የተለየ ስጦታ ነው። የእሱ ታሳቢነትም ለአሕዛብ የምስክርነት ኑሮ መኖር ነው። እስራኤል በዚህ አልሆነለትም! ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የያህዌ ዘላለማዊ የማዳን ዕቅድ።

ዩቢኤስ የጽሑፍ ፕሮጀክት ይሄንን ሐረግ "ሐ" ደረጃ ነው የሚሰጠው (ሁነኛ ጥርጣሬ)። እሱም የሚያመለክተው ከአእመቅ በተቃራኒው ነው፣ "እንዲያውቁ አላደረጋቸውም።" ይህ ልዩነት የሚሆነው
1. ኤምቲ፣ አእመቅ – לב - םועדי
2. አእመቅ፣ የተእመቅ– לב - םעידי

**147:20ሐ** መዝሙሩ የሚጠናቀቀው እንዳጀማመሩ ነው — "ሃሌ ሉያ"!

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝ. 145፡6፤8-13 እንዴት ታብራራዋለህ፣ "ሰዎች ሁሉ" በሚለው ላይ በማተኮር፣ እና 147ን እስራኤል ላይ በማተኮር (በተለይም፣ መዝ. 147፡19-20)?
2. መዝ. 147፡4 ከሥነ-መለኮት አኳያ በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) መቼት እጅግ ጠቃሚ የሚሆነው ለምንድነው?
3. መዝ. 147፡7-9 ከሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30 ጋር የሚዛመደው እንዴት ነው?
4. የእግዚአብሔር የመጋቢነት ክብካቤ መዝ. 147፡16-18 ላይ ተገልጿል፣ ለተፈጥሮ ቋሚነት ያለው ፈርጅ በመስጠት። ይህም በምዕራባውያን ባህል ባለው የ"ሳይንሳዊ ዘዴ" እድገት ላይ እንዴት ተጽዕኖውን ያሳድራል?
5. መዝ. 147፡20 የሚያመለክተው እግዚአብሔር ራሱን ወይም ራዕዩን ለአሕዛብ እንደማያካፍል ነውን?

# መዝሙር 148
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| ፍጥረት ሁሉ ጌታን እንዲያመሰግን ጥሪ ቀርቦለታል<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | ምስጋና ለጌታ ከፍጥረቱ | የውዳሴ ጥሪ የተፈጠረ ነገር ሁሉ ጌታን እንዲያመሰግን | ጥሪ ለዩኒቨርስ ጌታን እንዲያመሰግን | ዩኒቨርሳዊ የምስጋና ውዳሴ |
| 148:1-6 | 148:1ሀ | 148:1-2 | 148:1ሀ | 148:1-2 |
| | 148:1ለ-4 | | 148:1ለ-2 | |
| | | 148:3-4 | 148:3-4 | 148:3-4 |
| | 148:5-6 | 148:5-6 | 148:5-6 | 148:5-6 |
| 148:7-12 | 148:7-12 | 148:7-8 | 148:7-8 | 148:7-8 |
| | | 148:9-10 | 148:9-10 | 148:9-10 |
| | | 148:11-12 | 148:11-12 | 148:11-12 |
| 148:13-14 | 148:13-14መ | 148:13-14 | 148:13-14ሐ | 148:13-14 |
| | 148:14ሠ | | 148:14መ | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. መጽሐፍ ቅዱስ ምድር-ተኮር መጽሐፍ መሆኑን አስታውስ። ይህ ዓለም እግዚአብሔር ያዘጋጀው ልዩ ስፍራ አትኩሮት ነው፣ ከላቀ ፍጡሩ ጋር ላለ ኅብረት (ማለትም፣ በእርሱ መልክና አምሳል ለተሠራው፣ ዘፍ. 1፡26-27)።

ለ. የተለያየ ደረጃ ያለው ፍጥረት ሁሉ
1. ሰማያዊ (ማለትም፣ "ከሰማያት፣" መዝ. 148፡1ለ)
2. ምድራዊ (ማለትም፣ "ከምድር፣" መዝ. 148፡7ሀ)
3. የኪዳኑ ሕዝብ

ጥሪ ተደርጎላቸዋል፣ ያህዌን እንዲያመሰግኑ፣ የሕይወት ሁሉ ፈጣሪና መጋቢ፣ ለዚህ ዓለምና ከዚህ ዓለም ጋር በተያያዘ (ማለትም፣ መላእክት)።

ሐ. ይህ የሰማይና የምድር፣ ሕይወት ያለውና የሌለው ኅብረ-ዘማሪ ነው!

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡148፡1-6**
[1]**ሃሌ ሉያ።**
**እግዚአብሔርን ከሰማያት አመስግኑት**

| |
|---|
| በአርያም አመስግኑት። <br> [2]መላእክቱ ሁሉ፥ አመስግኑት <br> ሠራዊቱ ሁሉ፥ አመስግኑት። <br> [3]ፀሐይና ጨረቃ፥ አመስግኑት <br> ከዋክብትና ብርሃን ሁሉ፥ አመስግኑት። <br> [4]ሰማየ ሰማያት፥ አመስግኑት <br> የሰማያት በላይም ውኃ። <br> [5]እርሱ ብሎአልና፥ ሆኑም እርሱም አዝዞአልና፥ ተፈጠሩም <br> የእግዚአብሔርን ስም ያመስግኑት። <br> [6]ለዘላለም ዓለም አቆማቸው <br> ትእዛዝን ሰጠ፥ አያልፉምም። |

**148፡1-6** "አመስግኑ" የሚለው ግሥ (ቢ.ዲ.ቢ. 237፣ ኬ.ቢ. 248) በዚህ መዝሙር ላይ በብዛት አለ። ሦስቱም አንጓዎች እያንዳንዳቸው በእርሱ ነው የሚጀምሩት። መዝሙር 148:1-4 ሁሉንም ፔል ተተኳሪዎች ይዟል፣ መዝ. 148:7፣14 እንዳለው ሁሉ።

ይህ የመጀመሪያ አንጓ የሚያተኩረው "ከምድር በላይ" ባሉት ነገሮች ነው (መዝ. 103:19-22)።

1. "ከሰማያት (ቢ.ዲ.ቢ. 1029) — ይህ የሚያመለክተው ከምድር በላይ ያለውን ከባቢ አየር ነው፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማይ፣ እንዲሁም መዝ. 69:34፤96:11፤ኢሳ. 44:23፤49:13 እይ
2. "በአርያም" (ቢ.ዲ.ቢ. 928) – ይህ ከ "ሰማይ" ጋር ትይዩ ነው
3. "መላእክቱ ሁሉ" (ቢ.ዲ.ቢ. 521) – ይህ የሚጠቅሰው የእግዚአብሔርን ንቁ አገልጋዮች ነው (መዝ. 103:20)፤ እነርሱ በተለየ የብኪ ጽሑፍ እንደተፈጠሩ አልተጠቀሰም፣ ነገር ግን እዚህጋ መካተታቸው በብርቱ ያሳያል፣ ቆላ. 1:16 ደግሞ ይሄንን ሐቅ አስረግጦ ያሳያል ሦስት ልዩ ርዕሶች አሉ፣ ከመላእክት ጋር በተያያዘ፡
   ሀ. ልዩ ርዕስ፡ የእግዚአብሔር መልአክ
   ለ. ልዩ ርዕስ፡ መላእክት እና አጋንንት
   ሐ. ልዩ ርዕስ፡ መላእክታዊ እርከኖች በጳውሎስ ጽሑፎች
4. "ሠራዊቱ ሁሉ" (ቢ.ዲ.ቢ. 838) — ይህ ቃል በሁለት መልኩ ጥቅም ላይ ይውላል
   ሀ. በወታደራዊ ዐውደ-ጽሑፎች እሱ የሚያመለክተው የመላእክትን ሰማያዊ ሠራዊት ነው
   ለ. በአስትራት አምልኮ ዐውደ-ጽሑፍ እሱ የሚያመለክተው በሰማይ ላይ ያሉትን ብርሃናት ነው (ማለትም፣ ፀሐይ፣ ጨረቃ፣ ከዋክብት፣ ተወርዋሪ ኮከቦች) እነርሱም አማልክት ናቸው ተብሎ የሚታሰቡ ፣ በሰው ሕይወት ላይ ተጽዕኖቸውን የሚያሳድሩ፤ "ሀ" ከመዝ. 148፡2ሀ ሊዛመድ እንደሚችል ወይም "ለ" ከመዝ. 148፡ 3 (መዝ. 103፡21) ሊዛመድ እንደሚችል ተገንዘብ
5. "ፀሐይ እና ጨረቃ" — እነዚህ ታላቅ ብርሃናት ናቸው የዘፍ. 1:14-16፤ ሁለቱም በጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ይመለኩ ነበር፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ የጨረቃ አምልኮ
6. "ከዋክብትና ብርሃን ሁሉ" — ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 147፡4 ላይ
7. "የሰማያት በላይ" — ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሰማያት እና ሦስተኛው ሰማይ
8. "የሰማያት በላይም ውኃ" — ይህ የሚጠቅሰው ዘፍ. 1:6-8 ነው፤ እግዚአብሔር የጥንቶቹን ውኆች ተቆጣጥሯል፤ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ውኆች

**148፡5ሀ "ያመስግኑት"** ይህ ፔል ያልተጠናቀቀ ነው፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ። እሱም የሚገልጸው ለፈጣሪ የሚደረግ ጸሎት/ምስጋና ጥሪ ነው (መዝ. 148፡5ለ-6)።

"ስም" የቆመው ለያህዌ ለራሱ ነው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ "ስሙ" የያህዌ።

**148፡5ለ** ይህ የሚጠቅሰው ፍጥረትን ነው፣ በዘፍጥረት 1 የንግግር ቃል (መዝ. 33:6፣9፤ዕብ. 11:3)።

**148፡6** ይህ ግነታዊ ዓረፍተ-ነገር ነው፣ የዚህን ዓለምና የእሱን ወቅቶች ጽኑዕነት የሚያሳይ (ኤር. 31:35-36፤33:20፣25)። ከ2 ጴጥ. 3:7፣10-12 እንደምንረዳው የተበከለው፣ የወደቀው ፍጥረት ይጸዳል። ከሳይንስ፣ ዘመናዊዎቹ ያውቃሉ፣ የምንኖረው በሚናወጥ፣ ባልተረጋጋ ዩኒቨርስ ውስጥ መኖራችንን። ይህ የፀሐይ ሥርዓት ዘላለማዊ አይደለም። እነዚህ የእምነት መግለጫዎች ናቸው፣ ለእግዚአብሔር ዘላለማዊነት (መዝ. 93:1፤ 96:10መ) እና የእርሱ ተስፋ፣ እርሱን የሚያውቁት ከእርሱ ጋር እንደሚሆኑ!

▣ **"ለዘላለም ዓለም"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ዘላለም (ኦላም)።

▣

| | |
|---|---|
| **አአመመቅ፣ አኪጀቅ** | **"የማያልፍ ትእዛዝ"** |
| **አየተመቅ** | **"እሱም የማያልፉትን ትእዛዝ አደረገ"** |
| **አኢመቅ** | **"በማይለወጥ ትእዛዝ"** |

ይህ ሐረግ የሚያመለክተው

1. የእግዚአብሔርን ትእዛዝ/ዕቅድ (መዝ. 33:11)
2. እግዚአብሔር ያበጀው የምድር/ባሕር/ወንዞች ወሰን (ኢዮብ 38:8-11፤መዝ. 104:9፤ኤር. 5:22)

"በላይ ማለፍ፣" "በውስጥ ማለፍ፣" "በማለፍ፣" "ማለፍ" የሚሉት ግሦች (ቢ.ዲ.ቢ. 716፣ ኬ.ቢ. 778፣ ቃል ያልተጠናቀቀ) በግልጽ እንደሚታየው ሰፊ የፍች መስክ አላቸው፣ ቁ. 1ን ወይም ቁ. 2ን የሚደግፉ።

**መዝሙር ፡148፡7-12**

[7]እባቦች ጥልቆችም ሁሉ፥
እግዚአብሔርን ከምድር አመስግኑት
[8]እሳትና በረዶ አመዳይና ውርጭ፥
ቃሉን የሚያደርግ ዐውሎ ነፋስም
[9]ተራሮች ኰረብቶችም ሁሉ፥
የሚያፈራም ዛፍ ዝግባም ሁሉ
[10]አራዊትም እንስሳትም ሁሉ፥
ተንቀሳቃሾችም የሚበርሩ ወፎችም
[11]የምድር ነገሥታት አሕዛብም ሁሉ፥
አለቆች የምድርም ፈራጆች ሁሉ፥
[12]ጕልማሶችና ቈነጃጅቶች፥
ሽማግሌዎችና ልጆች

**148፡7-12** ይህ አንጓ የሚያተኩርበት ሐረግ (አንድ ግሥ ይሸፍናል መዝ. 148፡7-12፣ እያንዳንዱን መስመር "ምስጋና" በሚል) በዚህ ምድር ላይ በሚኖሩ ሕይወት ባላቸው ነገሮች ምስጋና ነው።

1. "የባሕር እባቦች" (ቢ.ዲ.ቢ. 1072)— ይህም በብዙ መልኩ ጥቅም ላይ ይውላል
   ሀ. እባብ – ዘጸ. 7፡9፣10፣12፤ዘዳ. 32:33፤መዝ. 91:13
   ለ. ዘንዶ – ኤር. 51:34 (ደግሞም የደጁ ስም መሆኑን ተመልከት ነህ. 2:13 ላይ)
   ሐ. የባሕር እባቦች — ድረ-ገጽ ቀጥታ ማስታወሻ ተመልከት ዘፍ. 1፡21፤ ኢሳ. 27፡1 ላይ
2. "ጥልቆችም ሁሉ" (ቢ.ዲ.ቢ. 1062)— ይህ በብዙ መልኩ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል
   ሀ. ከምድር በታች ያለ ውኃ (ጨውማ)፣ ዘፍ. 7:11፤8:2፤ኢዮብ 28:4፤38:16፤መዝ. 33:7፤107:23-26፤135:6፤ኢሳ. 51:10፤አሞጽ 7:4
   ለ. ንጹሕ ውኃ – ዘወትር ቀይ ባሕርን በማቋረጥ የሚጠቀስ፣ ዘጸ. 15:5፣8፤መዝ. 77:17፤78:15፤106:9፤ኢሳ. 63:13
   ሐ. የጥንት ውኆች – ዘፍ. 1:2፤መዝ. 104:6-7፤ምሳ. 8:27፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ውኆች (ውኃ ወደ ሕላዌ እንደ መጣ ፈጽሞ አልተነገረም፣ ዘፍጥረት 1 ላይ)
   መ. ሲኦል — መዝ. 71፡20 (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ሲኦል)
3. መዝሙር 148፡7-8 የምድርን የአየር ሁኔታና መልክዓ-ምድራዊ ገጽታዎችን ይዘረዝራል
4. መዝሙር 148፡10 የተፈጠሩትን የእንስሳት ሕይወት ሁሉ ይሸፍናል
5. መዝሙር 148፡11-12 በሁሉም ማኅበራዊ ደረጃና ዕድሜ ያሉትን የሰው ልጆች ሁሉ ይዘረዝራል

**መዝሙር ፡148፡13-14**

[13]የእግዚአብሔርን ስም ያመስግኑ
ስሙ ብቻውን ከፍ ከፍ ብሎአልና፥
ምስጋናውም በሰማይና በምድር ላይ ነው።
[14]የሕዝቡንም ቀንድ ከፍ ከፍ ያደርጋል
የቅዱሳኑንም ሁሉ ምስጋና
ወደ እርሱ ለቀረበ ለእስራኤል ልጆች ሕዝብ ከፍ ከፍ ያደርጋል።
ሃሌ ሉያ።

**148፡13-14** ይህ አንጓ የሚጀምረው እንደ መዝ. 148፡5 ነው፣ ከፔይል ያልተጠናቀቀ "ምስጋና" ጋር፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ። እሱም የሚያተኩረው ለያህዌ ስለሚገባው ምስጋና ነው፣ ከኪዳኑ ሕዝብ።

**148፡13 "ስሙ ብቻውን ከፍ ከፍ ብሎአልና፥"** ይህ

1. የአሀዳዊነት ጽሑፋዊ መግለጫ (ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ አሀዳዊነት (በአንድ አምላክ ማመን)
2. ያህዌን ከሰው ልጅ ጋር በንጽጽር (በተቃርኖ) ማስቀመጫ መንገድ (ኢሳ. 2፡11፣ 17)

▣ **"ክብር"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ክብር (ካቦድ፣ ብኪ)።

**148፡14 "ቀንድ"** ዕብራውያን የእንስሳትን ቀንዶች የሚመለከቱት (በተለይም፣ "በሬ፣" ዘዳ. 33:17፤መዝ. 92:10) እንደ ሥልጣን መግለጫ ነው (መዝ. 18፡2)።

1. በመቅደስ ያሉት መሠዊያዎች ቀንዶች አሏቸው
2. የሰው ሕይወት ባሕርይ የሚደረገው እንደ "ቀንድ" ዓይነት ነው
   ሀ. ከፍ ይላል (1 ሳሙ. 2:1፤መዝ. 89:17፣24፤92:10፤112:9)
   ለ. በመሬት ላይ ይኖራል (ኢዮብ 16:15)
   ሐ. ይወገዳል (መዝ. 75:10)

**148:14 "ቅዱሳኑም ሁሉ"** መዝ. 16:10 እና 145:10 ላይ ማስታወሻ ተመልከት፣ ድረ-ገጽ ላይ።
እዚህጋ ሐረጉ "የእርሱ ሕዝብ" ከሚለው ጋር ትይዩ ነው። እነርሱም በተጨማሪ ባሕርይ የሚያደርጉት

1. እንደ እስራኤል ልጆች
2. ወደ እርሱ እንደ ቀረቡ ሰዎች — ይህ በቅድሚያ የሚያመለክተው ካህናትን/ሌዋውያንን ነው፣ በመቅደስ የሚያገለግሉትን፣ ኋላ ላይ ግን ያህዌን ለሚያመልኩ ለሁሉም የኪዳን ሕዝቦች ጥቅም ላይ ውሏል

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት _መመሪያ_ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. መዝ. 148፡1-6 ከመዝ. 148፡7-12 ጋር እንዴት ይዛመዳል።
2. “ሠራዊት” የሚለውን፣ መዝ. 148፡2ለ ላይ አብራራ። እሱስ ከመዝ. 148፡2ሀ ወይም 149፡3 ጋር ይዛመዳልን?
3. አንዱ መዝ. 148፡6ን ከ2 ጴጥ. 3፡7፣10-12 ጋር እንዴት ያስታርቃል (ያስተያያል)?
4. “የባሕር እባቦች” የሚለውን መዝ. 148፡7ለ ላይ ያለውን ግለጽ።
5. መዝ. 148፡14 የሚያመለክተው ለእስራኤል ወይስ ለያህዌ የሚደረግ “ምስጋና” ነውን?

# መዝሙር 149
## የአዲሶቹ ትርጉሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| እስራኤል ጌታን እንዲያመሰግን ሲጠየቅ<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | ምስጋና ለእግዚአብሔር ስለ ማዳኑና ፍርዱ | ውዳሴ የበዓል ውዝዋዜን በማጀብ | የምስጋና ውዳሴ | የድል መዝሙራት |
| 149:1-4 | 149:1ሀ | 149:1-9 | 149:1ሀ | 149:1ሀ |
| | 149:1ለ-ሐ | | 149:1ለ-9ለ | 149:1ለ-3 |
| | 149:2-4 | | | |
| | | | | 149:4-6 |
| 149:5-9 | 149:5-9ለ | | | |
| | | | | 149:7-9ለ |
| | 149:9ሐ | | 149:9ሐ | |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ሦስተኛው አንቀጽ
4. ወዘተርፈ

## ዐውደ-ጽሑፋዊ ይዘት

ሀ. ይህ መዝሙር የተጻፈው ለእስራኤል ወታደራዊ ድል ነው፣ በአሕዛብ ጠላት ላይ፣ ለመታሰቢያና ለደስታ (መዝ. 149፡6ለ-9ሀ)።

ለ. እስራኤል ክብር አግኝቷል፣ እንደ ያህዌ የተለየ ሕዝብ (መዝሙር 112)።
1. የጻድቃን ጉባኤ ("የታማኞች ጉባኤ") – ቢዲቢ 874 አወቃቀር ቢዲቢ 339፣ መዝ. 149:1
2. ያህዌ የእነርሱ
   ሀ. ሠሪ ነው (ቢዲቢ 793 I፣ ኬቢ 889፣ ቃል አንቀጽ)፣ መዝ. 149:2
   ለ. ንጉሥ ነው (ቢዲቢ 572 I)፣ መዝ. 149:2
3. የእርሱ ሕዝቦች ... የተነሳቀሉት፣ መዝ. 149፡4
4. ቅዱሳን ("ታማኞች")፣ መዝ. 149፡5
5. "ቅዱሳኑ" ("የታመኑት")፣ መዝ. 149፡9

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር ፡149፡1-4**
**1ሃሌ ሉያ።**
**ለእግዚአብሔር አዲሱን ቅኔ ተቀኙለት**
**ምስጋናው በቅዱሳኑ ጉባኤ ነው።**
**2እስራኤል በፈጣሪው ደስ ይበለው፥**
**የጽዮንም ልጆች በንጉሣቸው ሐሤትን ያድርጉ።**
**3ስሙን በዘፈን ያመስግኑ፥**

**በከበሮና በመሰንቆም ይዘምሩለት።**
**[4]እግዚአብሔር በሕዝቡ ተደስቶአልና፥**
**የዋሃንንም በማዳኑ ከፍ ከፍ ያደርጋልና።**

**149፡1-4** አንጓው የሚጀምረው በሁለት ትይዩ ፔይል ተተኳሪዎች ነው።

1. አመስግኑ
2. ዘምሩ

እነዚህንም ሦስት ተለጣጣቂ ያልተጠናቀቁዎች ይከተሏቸዋል፣ በተጽዕኗዊ ጥቅም ላይ የዋሉ።

1. እስራኤል ደስ ይበለው
2. ጽዮን ሐሴት ታድርግ
3. ስሙን ያመስግኑ
4. ምስጋናም ይዘምሩለት

መዝሙረኛው የሚጸልየው እስራኤል በወታደራዊ ድሉ ተገቢ ምላሽ እንዲሰጥ ነው፣ እሱም ከያህዌ እንደ ሆነ እውቅና በመስጠት፣ ከራሳቸው ሳይሆን።

**149፡1 "አዲስ ዝማሬ"** ይህ የሚወክለው አንድን ሁነት ለማሰብ (ለመዘከር) ባህላዊ ዘዴ ነው (ከ ዘጸ. 15፡1-18፤21፤መሳ. 5፡1-13፤1 ሳሙ. 18:6፤መዝ. 33፡3፤40፡3፤96፡1፤98፡1፤ኢሳ. 42፡10 ጋር አነጻጽር)።

▣ **"ጉባኤ"** ይህ *ቃሀል* ነው (ቢዲቢ 874)፣ እሱም በ LXX፣ *ኢክሌሲያ* በሚል የተተረጎመ። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቤተ-ክርስቲያን (*ኢክሌሲያ*)።

▣ **"ቅዱሳኑ"** ይህ ተመሳሳይ ቃል ነው፣ መዝ. 148፡14 ላይ ጥቅም ላይ የዋለ፣ እሱም ከ*ሄሰድ* የመጣ (ቢዲቢ 339)። ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 16፡10 ላይ በድረ-ገጽ ቀጥታ መስመር።

**149፡2 "ፈጣሪ"** ይህ (ቢዲቢ 793 I) ፍጥረትን አያመለክትም፣ ነገር ግን የአብርሃምን መጠራት እና ለዘሩ የተሰጠውን ተስፋ እንጂ፣ እሱም በሙላት የጸደቀ፣ ሲና ተራራ ላይ (ዘጸአት 19-20)። እሱም ደግሞ መዝ. 95፡6፤100፡3፤ ኢሳ. 17፡7 ተጠቅሷል)። ያህዌ በተለየ መልኩ የእነርሱ ፈጣሪ፣ አዳኝ፣ እና ኪዳናዊ አምላክ ነው!

▣ **"ንጉሣቸው"** ይህ ሥነ-መለኮታዊ መረዳት ወደ ኋላ ተመልሶ ወደ 1 ሳሙ. 8፡7፣ መዝ. 47፡6፤89፡18 ይሄዳል። የእግዚአብሔር ሕዝብ ንጉሥ ማለት የእርሱ ምድራዊ ተወካይ ነው፣ የእርሱ የበታች የበጎች እረኛ።

▣ **"ጽዮን"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ጽዮን።

**149፡3 "በዘፈን"** ይህ የሚያመለክተው የተለየ የአምልኮ ሁነት አከባበር ነው

1. ወታደራዊ ድል (ዘጸ. 15፡20፤መሳ. 11፡34፤1 ሳሙ. 18፡6)
2. የአምልኮ ሁነት (2 ሳሙ. 6፡5፤መዝ. 150፡4)
3. መታደስ (መዝ. 30፡11፤ከዚህ ጋር በተያያዘ፣ "አልጋ" [ቢዲቢ 1012] የሚያመለክተው ታማሚ ሰዎች የሚተኙበት ስፍራ ነው፣ ዘጸ. 21፡18፤ ኢዮብ 33፡19)

**149፡4 "ጎስቋሎች"** ምንም እንኳ ይህ ሥር (ቢዲቢ 776) ድህና ችግረኛን የሚጠቅስ ቢሆንም፣ እሱ ዘወትር ጥቅም ላይ የሚውለው በስደት ላይ ላለው የእግዚአብሔር ሕዝብ ነው።

▣ **"ድኅነት"** ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ድኅነት/መዳን (ብኪ) ።

## መዝሙር ፡149፡5-9

**[5]ቅዱሳን በክብር ይመካሉ**
**በምንጣፋቸውም ላይ ሐሤትን ያደርጋሉ።**
**[6]የእግዚአብሔር ምስጋና በጉሮሮአቸው ነው**
**ሁለት አፍ ያለውም ሰይፍ በእጃቸው ነው፥**
**[7]በአሕዛብ ላይ በቀልን**
**በሰዎችም መካከል ቅጣትን ያደርጉ ዘንድ**
**[8]ንጉሦቻቸውን በሰንሰለት፥**
**አለቆቻቸውንም በእግር ብረት ያስሩ ዘንድ**
**[9]የተጻፈውን ፍርድ ያደርጉባቸው ዘንድ።**
**ለቅዱሳን ሁሉ ይህች ክብር ናት።**
**ሃሌ ሉያ።**

**149፡5-9** ይህ አንጓ ሦስት የጸሎት ጥያቄዎች አሉት፣ ያልተጠናቀቁትን በመጠቀም፣ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋሉ።

1. ከፍ ማድረግ

2. በደስታ መዘመር
3. ታሳቢ "የመሆን" ግሥ፣ መዝ. 149፡6ሀ ላይ

ይህ አንጓ ጸሎቱን የሚደባልቀው

1. የእግዚአብሔር ሕዝብ እንዲደሰት
2. የእግዚአብሔር ጠላቶች እንዲፈረድባቸው

**149፡5 "ቅዱሳን"** ይህ ከሄሰድ ሥር ነው (ቢዲቢ 339፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ምሕረት [ሄስድ])። እሱም ዘወትር ጥቅም ላይ ይውላል፣ የሚገልጸውም ለኪዳን ታማኝ የሆነ ሰውን ነው።

ሌለኛው ለታማኝ ተከታዮች ጥቅም ላይ የሚውለው ቃል ከ*ካዶሽ* ሥር ነው (ቢዲቢ 872፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቅዱስ)፣ እሱም ለያህዌ አገልግሎት የተለየ ሰውን የሚገልጽ ነው።

እነዚህ "ቅዱሳን" ኃጢአት-የለሾች አይደሉም፣ ነገር ግን እምነት፣ ታዛዥነት፣ እና ንስሐ የሚገባ ግንኙነት ከያህዌ ጋር አላቸው።

▣ **"ክብር"** ይህን የዕብራይስጥ ሥር (ቢዲቢ 458፣ ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ክብር [ካቦድ]) ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው። እሱም ሰፊ የፍች መስክ አለው። ኤቢ (ገጽ 357) የሚያስበው የያህዌ መጠሪያ እንደሆነ ነው፣ "የእነርሱ ባለ ክብር።"

▣ **"በምንጣፋቸውም ላይ ሐሤትን ያደርጋሉ።"** ይህ አስገራሚ ስፍራ ነው ለ "ከፍ ለማድረግ... ለመዘመር።" ይህ ዘይቤአዊ ቋንቋ መሆን አለበት፣ በደስታ፣ በሰላማዊ ልብ ሆኖ በመልካም ለሚተኛ ሰው! ይህ የመዝ. 6፡7 ተቃራኒ ነው።

እሱም በርግጥ ይቻላል (ቲንዳሌ፣ *ብኪ ሐተታ ተከታታይ*፣ ቅጽ 16፣ *መዝሙር*፣ ገጽ 527) "ምንጣፍ" የሚያመለክተው ለመመገብ መቀመጥን ነው፣ እና ስለዚህ፣ በድል ግብዣ ላይ መዘመርና መደሰት!

**149፡6** የመዝ. 149፡5 ሰላማዊ አዝማሚያ፣ ከወታደራዊ ዝግጅነት ጋር ይገጥማል። እዚህ ሰላም አለ፣ ምክንያቱም ያህዌ ለኪዳን ሕዝቡ ድልን ስለ ሰጠ፣ በአካባቢው ሕዝቦች ላይ (መዝ. 149፡7-8)።

▣ **"ታላቅ ምስጋና"** ይህ አወቃቀር (ቢዲቢ 928፣ ኬቢ 1206 እና ቢዲቢ 42) እዚህጋ ብቻ ነው የሚገኘው፣ እንዲሁም መዝ. 66፡17 ላይ።

▣ **"ሰይፍ በእጃቸው ነው"** ይህ ሐረግ የሚያመለክተው

1. ያለፈው ድል ምናባዊ ምስያ
2. ተምሳሌታዊ ዘፈን፣ በካህናት
3. ለሚመጣው ውጊያ መዘጋጀት

**149፡7** አንዳንዶች ይሄንን ቁጥር የሚመለከቱት በፍጻሜ ዘመን መቼት ነው፣ ነገር ግን እሱ ሊገጥም የሚችለው በእስራኤል ታሪክ ከማንኛውም ድል ጋር ነው፣ በአካባቢያቸው የጥቅም (ጥንታዊ ቅርብ ምስራቅ) ሕዝቦች ላይ።

▣ **"በቀል"** ለመልካም አጭር ማብራሪያ፣ ለዚህ ሥነ-መለኮታዊ ጽንሰ-ሐሳብ፣ ብኪ ላይ፣ ኒዶቲ ቅጽ 4 ገጽ 1140-1149 ተመልከት። ያህዌ በዚህ ሕይወት ላይ ፍርድን የማያመጣ ከሆነ፣ ከሞት በኋላ ላይ ይኖራል።

**149፡9ሀ "የተጻፈውን ፍርድ"** ይህ የሚያመለክተው

1. የ"ቅዱስ ጦርነት" ተስፋ፣ በዘጸአትና ድል በማድረግ ላይ እንዳለው
2. የ"ርግማንና በረከት" ተስፋ ውጤቶች፣ የሌዋውያን 26 እና ዘዳግም 27-30
3. የትንቢታዊ ክፍሎች ጠቃሽ፣ በአሕዛብ ላይ ስላለው ፍርድ (ማለትም፣ ኤርምያስ 46-51)
4. ለዚህ ዓይነቱ የ "ሰላም ተስፋ" የተሻለ ምሳሌ ሕዝ. 28፡26፤34፡25-28፤38፡8 ነው

**149፡9ለ** በያህዌ የተገኘው ድል ለኪዳን ሕዝቡ ክብርን ይሰጣል (መዝሙር 1121)።

**149፡9ሐ** መዝሙር 146-150 ሁሉም የሚጀምሩትና የሚያጠናቅቁት በ "ሃሌ ሉያ" ነው፣ ፔይል ተተኳሪ "የምስጋና"፣ ወይም የያህዌ ምሕጻረ-ቃል።

## የውይይት ጥያቄዎች

ይህ የጥናት <u>መመሪያ</u> ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው፡፡ እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል፡፡ ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ፡፡ ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው፡፡

እነዚህ የውይይት ጥያቄዎች የተሰጡት የዚህን መጽሐፍ ክፍል ዋና ዋና ጉዳዮች በሚገባ እንድታጤን እንዲረዳህ ነው። ይህም ማለት በተገቢው እንድታሰላስል ለማነሣሣት እንጂ በዚህ ብቻ እንድትወሰን አይደለም።

1. በምን ዓይነቱ ሁኔታዎች ላይ ነው "አዲስ ዝማሬ" የሚዘመረው?
2. መዝ. 149፡2ሀ የሚያመለክተው ዘፍጥረት 1ን ነው ወይስ ዘፍጥረት 12ን?
3. መዝሙሩ ስለ አለፈው ወታደራዊ ድል ነው ወይስ ስለ ወደፊቱ?

4. መጽሐፍ ቅዱስ እንደ አጠቃላይ አጽንዖት የሚሰጠው በአሕዛብ ላይ ስላለው ፍርድ ነው ወይስ ስለ አሕዛብ መካተት?
5. ቅዱሳን እነማናቸው፣ መዝ. 149፡1፤5፤9 ላይ?

# መዝሙር 150
## የአዲሶቹ ትርጒሞች የአንጓ ምድቦች

| አአመመቅ | አኪጀት | አየተመት | አእቅ | አኢመቅ |
|---|---|---|---|---|
| የምስጋና መዝሙር<br>ኤምቲ መግቢያ የለውም | ሁሉም ነገር ጌታን ያመስግን | የምስጋና ዝማሬ የመዝሙር ማጠቃለያ | ጌታን አመስግኑ | የማጠቃለያ ኅብረ ዝማሬ ምስጋና |
| 150:1-2 | 150:1ሀ | 150:1-2 | 150:1ሀ | 150:1ሀ |
| | 150:1ለ-ሐ | | 150:1ለ-2 | 150:1ለ-2 |
| | 150:2 | | | |
| 150:3-6 | 150:3-5 | 150:3-6 | 150:3-6ለ | 150:3-6ሀ |
| | 150:6ሀ | | | |
| | 150:6ለ | | 150:6ሐ | 150:6ለ |

**የንባብ ምድብ ሦስት ገጽ (ገጽ xvi ተመልከት በመግቢያው ክፍል)**
*የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ በየአንቀጹ ደረጃ መከተል*

ይህ የጥናት መመሪያ ትርጓሜ ሲሆን፣ ያም ማለት ግን መጽሐፍ ቅዱስን በግል ለምትተረጒመው ኃላፊነቱን ትወስዳለህ ማለት ነው። እያንዳንዳችን በተሰጠን ብርሃን መጓዝ ይኖርብናል። ቀዳሚዎቹ ተርጓሚዎች አንተ፣ መጽሐፍ ቅዱስና መንፈስ ቅዱስ ናችሁ። ይህንንም መልሰህ በተርጓሚው ላይ በሌላ አባባል እንዳትወስደው።

ምዕራፉን በአንድ ጊዜ አንብበው፡፡ ፍሬ ሐሳቦቹን ለይ (የንባብ ምድብ ቁ.3 ገጽ xvi)፡፡ ያንተን የፍሬ ሐሳብ ምድቦች ከላይ ከተዘረዘሩት አምስት ትርጓሜዎች ጋር አስተያይ፡፡ ሙሉው መገለጥ በአንቀጹ ላይ ሊገኝ ባይችልም የዋነኛውን ጸሐፊ ሐሳብ የሆነውን የትርጓሜው ዋና ነገር ይገኝበታል፡፡ እያንዳንዱ አንቀጽ አንድና አንድ ብቻ ፍሬ ሐሳብ ይዟል፡፡

1. የመጀመሪያው አንቀጽ
2. ሁለተኛው አንቀጽ
3. ወዘተርፈ

## የቃልና የሐረግ ጥናት

**መዝሙር፡150፡1-2**
**[1]ሃሌ ሉያ።**
**እግዚአብሔርን በመቅደሱ አመስግኑት**
**በኃይሉ ጠፈር አመስግኑት።**
**[2]በችሎቱ አመስግኑት**
**በታላቅነቱ ብዛት አመስግኑት።**

**150፡1-6** ብቸኛው ግሥ "ማመስገን" ነው (ቢ.ዲ.ቢ. 237፣ B 248) አስራ ሦስት ጊዜ ጥቅም ላይ የዋለ።.
1. አስራ ሁለት ፒይል ተተኳሪዎች (መዝሙር ላይ 146-150 ሠላሳ-ሦስት ጊዜ)
2. አንድ ፒይል ያልተጠናቀቀ በተጽዕኗዊ መልኩ ጥቅም ላይ የዋለ (መዝ. 150:6ሀ)

መስተጻምሮቹን ተገንዘብ።

1. በስፍራ
   ሀ. በመቅደሱ
   ለ. በኃይሉ ጠፈር
2. ምክንያቱም
   ሀ. ብርቱ ሥራው
   ለ. በታላቅነቱ ብዛት
3. በሙዚቃ መሣርያ (ምን ዓይነት እንደሆነ ዘወትር ግልጽ አይደለም)
   ሀ. መለከት (ቢ.ዲ.ቢ. 1051)
   ለ. በገና (ቢ.ዲ.ቢ. 490፣ 2 ሳሙ. 6:5)
   ሐ. መሰንቆ (ቢ.ዲ.ቢ. 614፣ 2 ሳሙ. 6:5)
   መ. ከበሮ (ቢ.ዲ.ቢ. 1074)

ሦ. የጅማት መሣርያዎች (ቢዲቢ 577 l)
ሸ. ዋሽንት (ቢዲቢ 721፣ ኒዶቲ፣ ቅጽ 3፣ ገጽ 334)
ቀ. ጸናጽል (ቢዲቢ 852፣ 2 ሳሙ. 6:5)
4. በዘፈን፣ መዝ. 150:4
5. በእስትንፋስ፣ መዝ. 150:6

**150:1** ይህ ቁጥር ጽሑፋዊ መንገድ ሊሆን ይችላል፣ መዝ. 150፡6ሀን ትይዩ የማድረግ።
"መቅደስ" (ማለትም፣ መቅደስ ወይም በምድር፣ መዝ. 148:7-12፤LXX "በቅዱሳኑ መካከል" የሚል አለው) ምድር እና "ጠፈር"ን የሚጠቅስ ነው (ሰማያዊ ዓለም፣ መዝ. 148:1-4)።
ሊሆን የሚችለው ሁለቱም መዝ. 150:1ለ እና 1ሐ የሚያመለክቱት የያህዌን (ሔል መዝ. 150:1ለ ላይ) መኖሪያ ነው (መዝ. 11:4)።

**150:2 "ብርቱ ድርጊቱ"** ማስታወሻ ተመልከት መዝ. 145:4፤5፤6፤7፤9፤12 ላይ።

**መዝሙር ፡150፡3-6**

**3በመለከት ድምፅ አመስግኑት**
**በበገናና በመሰንቆ አመስግኑት።**
**4በከበሮና በዘፈን አመስግኑት**
**በአውታርና በእምቢልታ አመስግኑት።**
**5ድምፁ መልካም በሆነ ጸናጽል አመስግኑት**
**እልልታ ባለው ጸናጽል አመስግኑት።**
**6እስትንፋስ ያለው ሁሉ እግዚአብሔርን ያመስግን፡-**
**ሃሌ ሉያ።**

**150፡3 "መለከት"** እነዚህ በካህናት የሚነፉ ናቸው። ልዩ ርዕስ ተመልከት፡ ቀንደ-መለከቶች፣ በእስራኤል ጥቅም ላይ የሚውሉ።

▣ **"በገናና መሰንቆ"** እነዚህ የሙዚቃ መሣርያዎች ናቸው፣ በሌዋውያን ጥቅም ላይ የሚውሉ፣ በመቅደስ አምልኮ (1 ዜና. 15:16፤2 ዜና. 29:25፤ነህ. 12:27)።

**150:6ሀ** እንዴት ያለው ያማረ ያገላለጽ መንገድ ነው፣ ሕይወት ስላላቸው ፍጥረታት (ሰው እና እንስሳ) ፈጣሪን ሲያመሰግኑ (መዝ. 103:19-22፤ 145:21፤148:7-12።

# ዕዝል አንድ — ዶክትሪናዊ/የእምነት መግለጫ

እኔ በተለየ መልኩ አይገደኝም፣ የእምነት መግለጫ ወይም ደንብ። ማጽናት የምመርጠው መጽሐፍ ቅዱስን ራሱን ነው። ሆኖም፣ የምረዳው የእምነት መግለጫ እኔን በደንብ ለማያውቁኝ ዶክትሪናዊ አስተሳሰቤን እንዲገመግሙ መንገድ ይሰጣቸዋል። በእኛ በርካታ ሥነ-መለኮታዊ ስሕተት እና መሳት ባለበት ዘመን፣ የሚከተለው አጭር ጭምቅ-ሐሳብ ቀርቧል፣ ስለ እኔ ሥነ-መለኮታዊ አቅርቦት።

1. መጽሐፍ ቅዱስ፣ ብሉይም ሆነ አዲስ ኪዳን፣ ተመስጧዊ የሆነ፣ የማይሳሳት፣ ሥልጣናዊ፣ ዘላለማዊ የእግዚአብሔር ቃል ነው። እሱ የእግዚአብሔር የራሱ መገለጥ ነው፣ በሰዎች የተመዘገበ፣ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ አመራር። እሱ ብቸኛው ግልጽ እውነት የሆነ ምንጭ ነው፣ ስለ እግዚአብሔርና ስለ ዓላማው። እሱ ደግሞ ብቸኛው የእምነትና የተግባር ምንጭ ነው፣ ለእርሱ ቤተ ክርስቲያን።

2. አንድ ብቻ ዘላለማዊ፣ ፈጣሪ፣ ተዋጂ (የሚቤዥ) አምላክ አለ። እሱ የሁሉም ነገሮች ፈጣሪ ነው፣ የሚታዩትም የማይታዩትም። እሱ ራሱን እንደ ወዳጅና እንደሚከባከብ አድርጎ ገልጿል፣ ብሎም እሱ ፍትሐዊና ትክክል ነው። እሱ ራሱን በሦስት በተለዩ አካላት ገልጿል፡ አብ፣ ወልድ፣ እና መንፈስ ቅዱስ፤ በርግጥ የተለያዩ ቢሆኑም በሐሳብ አንድ ናቸው።

3. እግዚአብሔር በንቃት ቃሉን እየተቆጣጠረ ነው። ዘላለማዊ ዕቅድ ለፍጥረቱ አለ፣ ሁለቱም የማይቀየር እና ግለሰብ-ተኮር የሆነ፣ እሱም የሰዎችን ነጻ ፍቃድ የሚፈቅድ። አንዳች ነገር ያለ እግዚአብሔር እውቅናና ፍቃድ አይሆንም፣ እናም እሱ የግለሰብ ምርጫዎችን ይፈቅዳል፣ በሁለቱም በመላእክትም ሆነ በሰዎች ዘንድ። ኢየሱስ በአብ የተመረጠ ሰው ነው፣ ሁሉም በእርሱ ብቃት በኩል ይመረጣሉ። የእግዚአብሔር የሁነቶች ቅድመ-እውቅና፣ የሰዎችን ቀድሞ የተጻፈ ጽሑፍ እንዲወስኑ ምርጫቸውን አይቀንስም። ሁላችንም ለሐሳባችንና ለድርጊታችን ኃላፊነት አለብን።

4. የሰው ልጅ፣ ምንም እንኳ በእግዚአብሔር መልክ ቢፈጠርና ከኃጢአት ነጻ ቢሆንም፣ በእግዚአብሔር ላይ ማመጽን መረጠ። ምንም እንኳ ከተፈጥሮ በላይ በሆነ ወኪል ቢፈተኑም፣ አዳምና ሔዋን በፍቃዳቸው ለሆኑት ራስ-ተኮርነት ኃላፊነት አለባቸው። ዓመጻቸው ሰዎችንና ፍጥረትን ጎዳ። እኛ ሁላችንም የእግዚአብሔር ምሕረት እና ጸጋ ያስፈልገናል፣ ለሁለቱም በአዳም ለተጠቃለለው (የወል) ሁኔታችን እና ለእኛ ግለሰባዊ የፍቃድ ዓመጻ።

5. እግዚአብሔር የይቅርታንና የመመለስን መንገድ አመቻችቷል፣ ለወደቀው ሰው። ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የእግዚአብሔር የተለየ ልጅ፣ ሰው ሆነ፣ ኃጢአት-የለሽ ሕይወትን ኖረ፣ እናም በተቀያሪነት ሞቱ በኩል፣ ስለ ሰው ልጅ ኃጢአት ቅጣት ተቀበለ። እሱ ብቸኛው መንገድ ነው፣ ለመመለስና ከእግዚአብሔር ጋር ላለ ኅብረት። ሌላ ምንም ዓይነት የመዳን መንገድ የለም፣ በእርሱ የተጠናቀቀ ሥራ ካለ እምነት በቀር።

6. እኛ እያንዳንዳችን በግለሰብ ደረጃ የእግዚአብሔርን የይቅርታና የመመለስ ስጦታ በኢየሱስ መቀበል ይኖርብናል። ይህንንም መቀዳጀት የሚቻለው በእግዚአብሔር ተስፋዎች በፍቃደኝነት በማመን ነው፣ በኢየሱስ በኩል፣ እና በፍቃደኝነት ከሚታወቅ ኃጢአት በመመለስ።

7. እኛ ሁላችንም ሙሉ ለሙሉ ይቅር ተብለናል፣ ተመልሰናልም፣ በክርስቶስ ባለን እምነት ላይ በመመሥረትና ከኃጢአት ንስሐ በመግባት። ሆኖም፣ የዚህ አዲስ ግንኙነት ማስረጃ የሚታየው በተለወጠ፣ በመለወጥ ላይ ባለ ሕይወት ነው። እግዚአብሔር ለሰዎች ያለው ግብ አንድ ቀን የሚሆን መንግሥተ-ሰማያት አይደለም፣ ነገር ግን አሁን ክርስቶስን መምሰል እንጂ። በእውነተኝነት የተዋጁት እነርሱ፣ ምንም እንኳ ባጋጣሚ ኃጢአት ቢሠሩም፣ በእምነትና በንስሐ ይቀጥላሉ፣ በሕይወታቸው ዘመን ሁሉ።

8. መንፈስ ቅዱስ "ሌላው ኢየሱስ" ነው። እሱም በዓለም ላይ አለ፣ የጠፉትን ወደ ክርስቶስ ለመምራት እና ክርስቶስን መምሰል በዳኑት ውስጥ ለማጎልበት። የመንፈስ ቅዱስ ስጦታዎች በደኅንነት ጊዜ ይሰጣሉ። እነርሱም የኢየሱስ ሕይወትና አገልግሎት ናቸው፣ ለአካሉ፣ ለቤተ-ክርስቲያን የተከፋፈሉ። ስጦታዎቹ በመሠረቱ የኢየሱስ ፍላጎት ዝንባሌና ሐሳብ ሲሆኑ፣ በመንፈስ ቅዱስ ፍሬ የሚነቃቁ ናቸው። መንፈስ ቅዱስ በዘመናችን ንቁ ነው፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ጊዜ እንደ ነበረው።

9. አብ ከሙታን የተነሣውን ኢየሱስ ክርስቶስን የሁሉም ነገር ዳኛ አደረገው። እሱም ወደ ምድር ይመለሳል፣ በሰው ልጅ ሁሉ ላይ ሊፈርድ። በኢየሱስ ያመኑትና ስሞቻቸው በበጉ የሕይወት መጽሐፍ ላይ የተጻፉ እነርሱ ዘላለማዊ የከበረ አካላቸውን ይቀበላሉ፣ እርሱ ሲመለስ። እነርሱም ከእርሱ ጋር ለዘላለም ይሆናሉ። ሆኖም፣ የእግዚአብሔርን እውነት ለመቀበል እምቢ ያሉ እነርሱ ለዘላለም ይነጠላሉ፣ በሦስትነቱ አንድ ከሆነው አምላክ ደስታ የተሞላበት ኅብረት። እነርሱም ከሰይጣንና ከመላእክቱ ጋር ይኮነናሉ።

ይህ በርግጥ የተጠናቀቀ ወይም በጥልቀት የሆነ አይደለም፣ ነገር ግን የልቤን አጠቃላይ ሥነ-መለኮታዊ ስሜት እንደሚሰጣችሁ ተስፋ አደርጋለሁ። መግለጫውን እወደዋለሁ፡

"በዋነኛ አስፈላጊነት — ኅብረት፣ በዳርቻዎች — ነጻነት፣ በነገሮች ሁሉ — ፍቅር።"